# የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት

## ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች

## ከጥቅምት 2017 እስከ የካቲት 2017 የተወሰኑ 239 የተጠቃለሉ የሰበር ችሎት ውሳኔዎች

**በአብዱራህማን ሰይድ**

**በፌደራልና ደቡብ ምእራብ ክልል ፍ/ቤቶች ጠበቃ እና በሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲ የህግ መምህር**

**ሐምሌ 2017**

**ሚዛን አማን፣ ኢትዮጵያ**

# በጥቅምት ወር 2017 የተወሰኑ
# <u>128</u> የሰበር ችሎት ውሳኔዎች

የሰ/መ/ቁጥር 213837

*ጥቅምት 08 ቀን 2017 ዓ/ም*

ዳኞች፡-እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች፡- አቶ ዘመረ ጀማነህ ቀረበ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አልማዝ አስፋው ከጠ ገነት ሰበኔ ጋር ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

# ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች በ03/11/2016 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት በቃለ መሃላ የተደገፈ አቤቱታ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 92999 በቀን 10/02/2012 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 244569 በቀን 15/04/2013 ዓ.ም የሻረው ቢሆንም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 200406 በቀን 21/11/2013 ዓ.ም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በመሻርና የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል ከወሰነ በኋላ ጉዳዩን በሰበር ያየው ይህ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ችሎት በዚህ መዝገብ በቀን 26/08/2014 ዓ.ም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት የወሰነ ቢሆንም የፌዴሬሽን ምክር ቤት በ6ኛ የፓርላማ ዘመን 3ኛ የስራ አመት 2ኛ መደበኛ ጉባኤ በመ.ቁ 804/16 በቀን 25/10/2016 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ በዚህ ሰበር ችሎት የተሰጠውን ውሳኔ የሻረው መሆኑን ይህ ችሎትና በተዋረድ የሚገኙ የስር ፍ/ቤቶች ተገንዝበው የአፈጻጸም ትዕዛዝ ይሰጥልኝ ብለው በመጠየቃቸው ሲሆን በስር ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ተጠሪ ሆነው ተጠሪ ደግሞ አመልካች ሆነው ጋብቻ እና ፍቺን በሚመለከት ጉዳይ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እንደሚከተለው አጠር አጠር ብሎ የተመለከተው ነው፡፡ ተጠሪ በስር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በቀን በ16/04/2011 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ ከአመልካች ጋር በ23/05/1957 ዓ.ም ባባህላዊ መንገድ ወይም ደግሞ በ29/05/1965 ዓ.ም በክብር መዝገብ ሹም ፊት ፈጽመውት የነበረው ጋብቻ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ልደታ ምድብ ችሎት በመ.ቁ. 142607 በቀን 01/11/2001 ዓ.ም በፍቺ እንዲፈርስና የንብረት ክፍፍል እንዲደረግ ከተወሰነ በኋላ የንብረት ክፍፍሉ በፍ/ቤት የክርክር ሂደት ላይ እያለ ጋብቻው በእርቅ እንዲቀጥልና ንብረታቸውንም የጋራ ለማድረግ ተስማምተው ክርክሩን አቋርጠው በትዳር ሲኖሩ የቆዩ መሆኑን ሆኖም ግን አሁን በመካከላቸው አለመግባባት የተፈጠረ መሆኑን በመግለጽ በመካከላችን ያለው ጋብቻ እንዲፈርስ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

አመልካችም በ27/05/2011 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ ከተጠሪ ጋር የነበረን ጋብቻ በቀን 01/11/2001 ዓ.ም በተሰጠ የፍ/ቤት ውሳኔ በፍቺ ፈርሶ ንብረት የተከፋፈልንና ከዚያ በኋላም ጋብቻ ፈጽመን አብረን ያልኖርን በመሆኑ፣ የፈረሰው ጋብቻ በድጋሚ ሊፈርስ የማይችል በመሆኑ፣ ተጠሪ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብትና ጥቅም የሌላቸው በመሆኑና ክሱ በድጋሚ የቀረበ በመሆኑ የተጠሪ አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚል መቃወሚያ አስቀድመው በፍሬ ነገር ክርክርም ግራ ቀኛችን ጋብቻችን ከፈረሰ በኋላ ባደረግነው የእርቅ ስምምነት እንደተመለከተው ቀድሞ የተደረገው ጋብቻ የፈረሰ ስለሆነ ግራ ቀኙ አዲስ ጋብቻ በመፈጸም አብሮ ለመኖር ተስማምተዋል የሚል ቃል ነበረው እንጂ በዚህ ቃል መሰረት አዲስ ጋብቻ አልፈጸምንም፡፡ በእርቅ ስምምነቱ የተጣሉትን ግዴታዎች ተጠሪ ባለመፈጸማቸው ጋብቻው ከፈረሰበት ጊዜ ጀምሮ ከተጠሪ ጋር በጋራ ኖረን የማናውቅ ሲሆን ሁለታችንም ያላገባ ማስረጃ አውጥተን ንብረት የተከፋፈልን በመሆኑ በመካከላችን ውጤት ያለው ጋብቻ ስለሌለ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃዎች መርምሮ ግራ ቀኙ የነበራቸው ጋብቻ በፍቺ መፍረሱ የተረጋገጠ ቢሆንም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ. 23021 በሰጠው ውሳኔ ጋብቻ ከፈረሰ በኋላ የቀድሞ ተጋቢዎች እንደገና አብሮ መኖር የትዳር ሁኔታ መኖሩን የሚያስገነዝብ ከሆነ ጋብቻ ስለመፈጸሙ የህግ ግምት መውሰድ የሚቻል ስለመሆኑ ትርጉም የሰጠበት ሲሆን አሁን በተያዘው ጉዳይ ግራ ቀኙ ጋብቻቸውን በእርቅ አድሰው የቀጠሉ ስለመሆኑና የትዳር ሁኔታ ያላቸው ስለመሆኑ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የተጠሪ ምስክሮች አስረድተዋል፡፡ የአመልካች ምስክሮች በበኩላቸው በእርቅ ስምምነቱ መሰረት ግራ ቀኙ አዲስ ጋብቻ ባለመፈጸማቸው ምክንያት ጋብቻው አልቀጠለም በማለት ይመስክሩ እንጂ ከላይ በሰበር ችሎቱ ከተሰጠው ትርጉም፣ ከቤተሰብ ህጉ አንቀጽ 96 እና የተጠሪ ምስክሮች ከሰጡት ምስክርነት አኳያ የትዳር ግንኙነቱ እንደገና አልቀጠለም ለማለት አያስችልም፡፡ የትዳር ግንኙነቱ የቀጠለ በመሆኑ ክሱ በድጋሚ የቀረበ ነው ወይም ተጠሪ መብትና ጥቅም የላቸውም ሊባል አይችልም፡፡ አመልካች ጋብቻ የለም ለማለት ያቀረቧቸው ክርክሮች ጋብቻ የለም ሊያስብሉ የሚችሉ ባለመሆናቸው በአመልካች የቀረበው መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክር ተቀባይነት አላገኘም፡፡ በመሆኑም በግራ ቀኙ መካከል ከቀን 24/08/2004 ዓ.ም ጀምሮ በእርቅ የቀጠለው ጋብቻ በዚህ ሁኔታ ሊቀጥል ስለማይችል ይህ ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በፍቺ ተቋርጧል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካችና ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅሬታ አድሮብናል በማለት በተለያየ መዝገብ ለፌ/ከፍ/ፍ/ቤት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም መዝገቦቹን አጣምሮ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ የግራ ቀኙ ጋብቻ በፍ/ቤት በተሰጠ ውሳኔ ከፈረሰ በኋላ በ24/08/2004 ዓ.ም የተደረገው እርቅ የሚያሳየው ግራ ቀኙ አዲስ ጋብቻ ለመፈጸም የተስማሙ መሆኑን ሲሆን በስምምነታቸው መሰረትም አዲስ ጋብቻ የፈጸሙ ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ የለም፤ ጋብቻው ከፈረሰበት ጊዜ በኋላ ግራ ቀኙ አብረው ያልኖሩ ስለመሆኑ የአመልካች ምስክሮች ያስረዱ ሲሆን ተጠሪም በህጉ ከተመለከቱት የጋብቻ አፈጻጸም ስርአቶች ውስጥ በአንደኛው ስርአት የተፈጸመ ጋብቻ ስለመኖሩ ያላስረዱ ስለሆነ በህግ ፊት ውጤት ያለውና ሊፈርስ የሚችል ጋብቻ የሌለ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ጋብቻው ይፍረስ በማለት የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪም በዚህ ውሳኔ ቅሬታ አድሮብኛል በማለት ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ በግራ ቀኙ መካካል የነበረው ጋብቻ እንዲፈርስ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ ግራ ቀኙ የነበራቸውን የንብረት ክፍፍል ክስ በመተው በጋብቻ ለመቀጠል ስምምነት አድርገው በትዳር የቆዩ መሆናቸው በማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ተጋብተው የነበሩ ባልና ሚስት ከፍቺ በኋላ በትዳር ሁኔታ አብረው ከቀጠሉ ባልና ሚስት ለመባል አዲስ ጋብቻ መፈጸም የማይጠበቅባቸው ስለመሆኑ ትርጉም የሰጠበት ከመሆኑ አኳያ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በህግ ፊት ውጤት ያለው ጋብቻ የለም በማለት የሰጠው ውሳኔ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቱ በ1965 ዓ.ም የተደረገውን ጋብቻ መሰረት አድርጎ መወሰን ሲገባው የእርቅ ስምምነት ያደረጉበትን ቀን መሰረት አድርጎ መወሰኑ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት ይግባኝ ሰሚ ከፍተኛ ፍ/ቤቱ የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቱ የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል ግራ ቀኙ በ23/03/1965 ዓ.ም

በክብር መዝገብ ሹም ፊት ያደረጉት ጋብቻ ይህ ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በፍቺ እንዲፈርስ ተወስኗል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካችም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት በ03/13/2013 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ለዚህ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ይህ ችሎትም ጉዳዩን መርምሮ ግራ ቀኙ ጋብቻቸውን ለመቀጠል ሚያዚያ 24 ቀን 2004 ዓ.ም ስምምነት አድርገው በትዳር የቆዩ ስለመሆኑ የተረጋገጠው ፍሬ ነገር በአመልካች ማስረጃ አለመስተባበሉ የተረጋገጠ በመሆኑና ይህ ችሎትም ማስረጃ የመመዘን ስልጣን የሌለው በመሆኑ በስር ፍ/ቤቶች ተጣርተው ተቀባይነት ያገኙትን ፍሬ ነገሮች ሊቀይራቸው ስለማይችል በሰበር መዝገብ ቁጥር 23021 በተሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ መሰረት በግራ ቀኙ መካካል ጋብቻ እንዳለ የህግ ግምት ተወስዶ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ ተገቢነት ያለው ሆኖ በመገኘቱ ጸንቷል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካችም በፍ/ቤቶቹ የተሰጠው ውሳኔ የህገ መንግስት ትርጉም ሊሰጥበት ይገባል በማለት አቤቱታቸውን ለህገ መንግስት አጣሪ ጉባዔ ያቀረቡ ሲሆን ጉባዔው መዝገቡን መርምሮ የህገ መንግስት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት በአብላጫ ድምጽ ውሳኔ የሰጠበት ቢሆንም የፌዴሬሽን ምክር ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ግራ ቀኙ ጋብቻቸው ከፈረሰ በኋላ አብረው መኖራቸው ጋብቻው እንደቀጠለ የሚያስቆጥር ነው የሚለው ትርጉም በህጉ ከተመለከቱት የጋብቻ አፈጻጸም ስርአቶች ውጭ በህግ አውጭው የማይታወቅ አዲስ የጋብቻ አፈፃፀም ስርአት የሚፈጥር በመሆኑ በሰበር ችሎቱም ሆነ በሌሎች የስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ትርጉም በህገ መንግስቱ አንቀጽ 55 ለህግ አውጭው የተሰጠውን ህግ የማውጣት ስልጣን የሚተላለፍ በመሆኑና በህጉ በተደነገጉት ሶስት የጋብቻ አፈጻጸም ስርአቶች መሰረት ያልተፈጸመን ጋብቻ ጋብቻ ነው ማለት ስለማይቻል የህገ መንግስት አጣሪ ጉባኤ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ችሎቶች የሰጡት ውሳኔ ሊሻር የሚገባው መሆኑን በማመልከት ወስኖ ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ይህንኑ ውሳኔ ያስፈጽም ሲል ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካችም በዚህ ትዕዛዝ መሰረት ውሳኔው ይፈጸምልኝ የሚል አቤቱታ አቅርበዋል፡፡በዚህ አቤቱታቸውም የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 92999 በቀን 10/02/2012 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 244569 በቀን 15/04/2013 ዓ.ም የሻረው ቢሆንም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 200406 በቀን 21/11/2013 ዓ.ም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በመሻርና የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል ከወሰነ በኋላ ጉዳዩን በሰበር ያየው ይህ ችሎት በዚህ መዝገብ በቀን 26/08/2014 ዓ.ም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት የወሰነ ቢሆንም የፌዴሬሽን ምክር ቤት በ6ኛ የፓርላማ ዘመን 3ኛ የስራ አመት 2ኛ መደበኛ ጉባኤ በመ.ቁ 804/16 በቀን 25/10/2016 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ በዚህ ሰበር ችሎት የተሰጠውን ውሳኔ የሻረው መሆኑን ይህ ችሎትና በተዋረድ የሚገኙ የስር ፍ/ቤቶች ተገንዝበው የአፈጻጸም ትዕዛዝ ይሰጥልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ተጠሪ በዚህ የአመልካች አቤቱታ ላይ አስተያየት እንዲሰጡበት በአድራሻቸው መጥሪያ ቢላክላቸውም ያቀረቡት አስተያየት ባለመኖሩ አስተያየት የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

ከላይ የተመለከተው በየደረጃው ባሉት የስር ፍርድ ቤቶች በግራ ቀኙ መካከል የተደረጉትን ክርክሮችና በየደረጃው ያሉት ፍርድ ቤቶች የደረሱበትን መደምደሚያ የሚያሳይ ሲሆን እኛም አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች በግራ ቀኙ መካከል የተደረጉትን ክርክሮችና በየደረጃው ባሉት ፍርድ ቤቶች ከተሰጡት ውሳኔዎችና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንፃር እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ክሳቸውን ያቀረቡት ከላይ እንደተመለከተው ከአመልካች ጋር በ23/05/1957 ዓ.ም ባባህላዊ መንገድ ወይም ደግሞ በ29/05/1965 ዓ.ም በክብር መዝገብ ሹም ፊት ፈጽመውት የነበረው ጋብቻ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ልደታ ምድብ ችሎት በመ.ቁ. 142607 በቀን 01/11/2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት በተሰጠ ውሳኔ በፍቺ እንዲፈርስ ተደርጎ የንብረት ክፍፍል እንዲደረግ የተወሰነ ቢሆንም የንብረት ክፍፍሉ በፍ/ቤት የክርክር ሂደት ላይ እያለ ጋብቻው በእርቅ እንዲቀጥልና ንብረታቸውንም የጋራ ለማድረግ የተስማሙ በመሆኑ ክርክሩን አቋርጠው በትዳር ሲኖሩ የቆዩ ቢሆንም በመካከላቸው አለመግባባት የተፈጠረ መሆኑን በመግለጽ በመካከላችን ያለው ጋብቻ እንዲፈርስ በመጠየቅ ቢሆንም ጉዳዩን በመጨረሻ የተመለከተው የፌዴሬሽን ምክር ቤት ግራ ቀኙ ጋብቻቸው በፍቺ ከፈረሰ በኋላ አብረው መኖራቸው ጋብቻው እንደቀጠለ የሚያስቆጥር ነው የሚለው ትርጉም በህጉ ከተመለከቱት የጋብቻ አፈጻጸም ስርአቶች ውጭ በህግ አውጭው የማይታወቅ አዲስ የጋብቻ አፈፃፀም ስርአት የሚፈጥር በመሆኑ በግራ ቀኙ መሀል በ29/05/1965 ዓም የተመሰረተው ጋብቻ በ01/11/2001 ዓም በፍቺ ከፈረሰ በኋላ የተፈፀመ ጋብቻ አለመኖሩን በማረጋገጥ መወሰኑ ጉዳዩን በይግባኝ በተመለከተው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረት በተጠሪ አቤቱታ መሰረት የሚሰጥ የፍቺ ውሳኔ የሌለ መሆኑን ያሳያል፡፡

ተጠሪ ከአመልካች ጋር የነበራቸው ጋብቻ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ልደታ ምድብ ችሎት በመ.ቁ. 142607 በቀን 01/11/2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት በተሰጠ ውሳኔ በፍቺ እንዲፈርስ ተደርጎ የንብረት ክፍፍል እንዲደረግ የተወሰነ ቢሆንም የንብረት ክፍፍሉ በፍ/ቤት የክርክር ሂደት ላይ እያለ ጋብቻው በእርቅ እንዲቀጥልና ንብረታቸውንም የጋራ ለማድረግ የተስማሙ መሆኑን ጠቅሰው ይኸው ግንኙነት ጋብቻ መሆኑ ተረጋግጦ ጋብቻው በፍቺ እንዲፈርስላቸው የጠየቁ መሆኑ የግኙነታቸው ሁኔታ (Status) የሚጣራ ሆኖ ግንኙነቱ በህግ አግባብ በሚሰጥ የፍቺ ውሳኔ እንዲረጋገጥ መጠየቃቸውን ያሳያል፡፡

በሰ/መ/ቁ.251411 እና በተመሳሳይ መዝገቦች የተሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም የመጨረሻው የዳኝነት ጥያቄ ተከራካሪ ወገኖቹ የንብረት ክፍፍልን አስመልክቶ የሚያድርጉትን ክርክር መነሻ ያደረገ በዚህ አግባብም ከጋብቻ በመለስ ያለው ግንኙነት ምን እንደሆነ ተጣርቶ ከንብረት ክርክሩ አንጻር ያለውን ውጤት አስመልክቶ ተገቢው ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩ ወደ ስር ፍርድ ቤት የተመለሰበት በመሆኑ የግንኙነታቸው

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ሁኔታ (Status) ተረጋግጦ የፍቺ ውሳኔ እንዲሰጥ በቀጥታ የቀረበ የዳኝነት ጥያቄ ባለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት ከቀረበው ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ ከሆነው አቤቱታ ጋር አንድ አይነት ይዘት ያለው (Squarely fit) ሆኖ አልተገኘም፡፡

ተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ ካቀረቡበት ነጥብ አንፃር መዝገቡን ስንመረምረውም ከላይ እንደተመለከተው የፌዴሬሽን ምክር ቤት በግራ ቀኙ መሀል በ29/05/1965 ዓም የተመሰረተው ጋብቻ በ01/11/2001 ዓም በፍቺ ከፈረሰ በኋላ የተፈፀመ ጋብቻ አለመኖሩን በማረጋገጥ መወሰኑ ጉዳዩን በይግባኝ በተመለከተው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረት በተጠሪ አቤቱታ መሰረት የሚሰጥ የፍቺ ውሳኔ የሌለ መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ ተከታዩን በአብላጫ ድምፅ ወስነናል፡፡

# ውሳኔ

1.የፌዴሬሽን ምክር ቤት በግራ ቀኙ መሀል በ29/05/1965 ዓም የተመሰረተው ጋብቻ በ01/11/2001 ዓም በፍቺ ከፈረሰ በኋላ የተፈፀመ ጋብቻ አለመኖሩን በማረጋገጥ የወሰነ በመሆኑ በተጠሪ አቤቱታ አግባብ የሚሰጥ የፍቺ ውሳኔ የለም ብለናል፡፡

2. ግራቀኙ በዚህ ችሎት ክርክር የደረሰባቸውን ወጭና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**ጉዳዩ ውሳኔ ስላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ/ጋ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

## የሃሳብ ልዩነት

ስሜ በተራ ቁጥር አምስት ላይ የተሰየምኩት ዳኛ በአብላጫው ሃሳብ የተለየሁበትን ምክንያት እንደሚከተለው አስፍሬያለሁ፡፡

ተጠሪ በ16/04/2011 ዓ/ም ጽፈው ባቀረቡት ክስ ከአመልካች ጋር ያላቸው ጋብቻ እንዲፈርስ ዳኝነት ጠይቀው ክርክሩ እስከ ፌዴሬሽን ምክር ቤት ደርሶ ግራቀኙ መጀመሪያ የነበራቸው ጋብቻ በ2001 ዓ/ም በፍርድ ቤት ከፈረሰ በኂላ መታረቅና ግንኙነቱን መቀጠላቸው በቤተሰብ ሕጉ ባለው ጋብቻ መፈጸሚያ ሦስት መንገዶች በአንዱ የተፈጸመ መሆኑን ስለማያሳይ ጋብቻ የለም ተብሎ ተወስኗል፡፡ ክርክሩን በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሰረት መምራት እና መቆጣጠር የፍርድ ቤቱ ኃላፊነት ሲሆን በተገቢው ሁኔታ ካልተመራ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ዓላማዎች የሆኑትን እንደ አንጻራዊ እውነትን የመፈለግ፣ ሥነ-ሥርዓታዊ ፍትህ፣ ክርክርን ውጤታማ፣ ወጭና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ መምራት የመሳሰሉትን ማሳካት ስለማይቻል የተከራካሪዎችን መብት ይነካል፡፡ ክርክር የሚወሰነው በተጠየቀው ዳኝነት አግባብ እንደሆነ የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 182(2) ላይ ተመልክቷል፡፡ ፍርድ ቤቱም ከቀረበው ዳኝነት አኳያ ከግራቀኙ ክርክር በመነሳት በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 246 እና ተከታዮቹ መሠረት በተነሱት ጉዳዮች ጭብጥ መስርቶ ውሳኔ የመስጠት ኃላፊነት አለበት፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ በቤተሰብ ሕጉ ዕውቅና ካላቸው ሁለት የግንኙነት ዓይነቶች ትልቅ የሆነውን በመጥቀስ በመካከላቸው ያለው ጋብቻ እንዲፈርስ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ጋብቻ የሚይዛቸው ፍሬ ነገሮች ጋብቻው መፈጸሙን የሚያሳይ ሥርዓት እና ባልና ሚስቱ አብረው በትዳር መኖርን ነው፡፡ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ጋብቻ ስለመፈጸሙ በተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 25-27 ከሦስቱ የጋብቻ መፈጸሚያ ሥርዓቶች በክብር መዝገብ ሹም ፊት፣ ባሕላዊ ወይም ሐይማኖታዊ ሥርዓት ስለመፈጸሙ አልተረጋገጠም በሚል ጋብቻ የለም ብሏል፡፡ ተጠሪ በክስ አቤቱታቸው አስቀድሞ ጋብቻ በፍርድ ቤት በ2001 ዓ/ም ከፈረሰበት ጊዜ ጀምሮ ክስ እስከቀረበበት 2011 ዓ/ም ድረስ በትዳር አብረን ኖረናል በሚል የገለጹ በመሆኑ በቤተሰብ ሕጉ ዕውቅና ካላቸው ግንኙነቶች ትልቁ የሆነው የጋብቻ ሥርዓት አልተፈጸመም ማለት ግራቀኙ አብረው አልኖሩም ማለት አይደለም፡፡ በ2001 ዓ/ም ጋብቻቸው በፍርድ ቤት ከፈረሰ በኂላ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በ24/08/2004 ዓ/ም አብረን ለመቀጠል እርቅ አድርገናል የሚለው የክስ ፍሬ ነገርም ይህን የሚጠቁም ነው፡፡ ይሕም እንደባልና ሚስት ለ10 ዓመት አብረው መኖራቸው የክስ ፍሬ ነገር አካል መሆኑን ያሳያል፤ ትልቁ ዳኝነት ተጠይቆ መረጋገጥ ካልቻለ በትልቁ ዳኝነት ሥር ያለው ሌሎች ዳኝነቶች እንደ አዲስ በሌላ መዝገብ እንዲቀርቡ ሥነ-ሥርዓ ሕጉ ዓላማ ይዞ የተቀረጸ አይደለም፡፡

የጋብቻ ሥርዓት አልተፈጸመመም ማለት ግራቀኙ እንደ ባልና ሚስት አብረው አልኖሩም ማለት አይደለም፤ በመካከላቸው ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብረው መኖር አለመኖራቸው እና ከኖሩም ሕጋዊ ውጤቱ እንዲወሰን ለሥር ፍርድ ቤት በጭብጥነት ተይዞ ሊመለስ ይገባ ነበር፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 251411 የተሰጠው ትርጉም ለዚህ ጉዳይ አስገዳጅ ነው፣ ሰበር ሰሚ ችሎቱ አስገዳጅ ትርጉሙ በግልጽ ሳይለወጥ የተለየ አቋም ላይ ሊደርስ አይችልም፡፡ ስለሆነም በአመልካችና በተጠሪ መካከል በክሱ በተጠቀሰው ጊዜ የጋብቻ ሥርዓት ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብረው መኖር አለመኖራቸው ላይ ክርክርና ማስረጃ ተሰምቶ ሊወሰን ሲገባ ይሕ አለመደረጉ የተጠሪን የንብረት መብት የሚጥስ ነው በማለት በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

እ/ጋ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መዝገብ ቁጥር፡- 226226

ጥቅምት 06 ቀን 2017 ዓም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካቾች፡- 1ኛ. አቶ ፈቀደ መኮንን
2ኛ. ሲ/ር ፈለቀች አንዳርጌ
3ኛ. አቶ ብርሀኑ በቀለ
} አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. ምዕራብ የገበያ አዳራሽ ኢ.ማ፡- ጠበቃ አሰፋ አሊ ቀረቡ

2ኛ. አቶ አምላኩ አበጀ፡- ቀረቡ

3ኛ. አቶ ናስር ሁሴን፡- አልቀረቡም

መዝገቡ በዳኞች የእረፍት ጊዜ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ፍርድ</u>**

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓለማአ የገለግልም!

ጉዳዩ የንግድ ማህበርን የሚመለከት ሆኖ ክሱ በቀረበበት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካቾች ከሳሽ ፣ ተጠሪዎች ደግሞ በተከሳሽነት ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾች ግንቦት 15 ቀን 2010 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- 1ኛ ተከሳሽ አ.ማ በ1986 ዓ.ም ተቋቁሞ እስከ 1995 ዓ.ም ድረስ በ2ኛ ተከሳሽ ስራ አስኪያጅነት ያለ ቦርድ ሲሰራ መቆየቱን፤ በታህሳስ 14 ቀን 1995 ዓ.ም በተሻሻለው መተዳደሪያ ደንብ ማህበሩ 12 የቦርድ አባለት እንዲኖረው መወሰኑን፤ማህበሩ ህዳር 10 እና 24 ፤ እንዲሁም ታህሳስ 22 ቀን ያደረገው ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባው በጋዜጣ ጥሪ ባለመደረጉ የንግድ ሚኒስቴር በድጋሚ እንዲደረግ ባዘዘው መሰረት መጋቢት 02 ቀን 2010 ዓ.ም ጉባኤ ተደርጎ በዚሁ ጉባኤ 12 እጩዎችን በማስመረጥ ሰባቱን ብቻ መርጦ ከሰባቱ ውስጥም ሶስቱ መስራት የማይችሉበትን ምክንያት በጽሁፍ አሳውቀው አራቱ ሁለተኛ እና ሶስተኛ ተከሳሾች፤ አቶ አለባቸው በላይ እና ወ/ሮ ፈለቀች ባህሩ የአስመራጭ ኮሚቴውን ቃለ-ጉባኤ ሳይዙ እና የተሻሻለውን መተዳደሪያ ደንብ ሳያቀርቡ ራሳቸው ተመርጠናል በማለት ታህሳስ 14 ቀን 2010 ዓ.ም ያስመዘገቡት ቃለ-ጉባኤ ሊሰረዝ የሚገባ መሆኑን፤2ኛ ተከሳሽ አክሲዮን ማኀበሩ ከተቋቋመ ጊዜ ጀምሮ በብቸኝነት የቦርድ አባልና ስራ አስኪያጅ ፣ 3ኛ ተከሳሽ ደግሞ የቦርድ አባልና ምክትል ስራ አስኪያጅ በመሆን ሲሰሩ የቆዩ ሲሆን በአሁኑ ስብሰባ ደግሞ 2ኛ ተከሳሽ የቦርድ ሰብሳቢ እና ስራ አስኪያጅ ፤ 3ኛተከሳሽ ደግሞ ምክትል ስራ አስኪያጅ እና የቦርድ አባል ሆነው የማህበሩን ስራ ጠቅልለው በመያዝ ከግዢ መመሪያ ውጪ ያለ ጨረታ እና ከተፈቀደላቸው ገንዘብ በላይ ወጪ በማድረግ በርካታ ግዢዎችን በመፈፀም ፤ የግንባታ ስራዎችን ያለ ዲዛይንና ፈቃድ ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቁ ስራዎችን ማከናወናቸውን ፤ ሁለተኛ ተከሳሽ ከብር 30,000.00(ሰላሳ ሺ) በላይ እንዳያንቀሳቅሱ በቦርድ ታግደው እያለ በርካታ ግዥዎችን በመፈፀም የማኀበሩን ጥቅም የሚጎዳ ተግባር መፈፀማቸውን ፤ ለሕንፃ ማስመረቂያ በቦርዱ ከተፈቀደላቸው ገንዘብ በላይ ወጪ በማድረግ ፤ የአልሙኒየም ስራ ያለ ጨረታ በማሰራት በሚሊዮን የሚቆጠር የማኀበሩን ገንዘብ አባክነዋል፤ የ2009 ዓ.ም ትርፍ ክፍፍል ማድረግ ሲገባቸው ባለማድረጋቸው በማኀበሩ እና ባለአክስዮኖች ላይ ከፍተኛ ጉዳት ማድረሳቸውን ገልጸው በመጋቢት 02 ቀን 2010 ዓ.ም የተመዘገበው ቃለ ጉባኤ እንዲሰረዝ፤ የ1ኛ ተጠሪ ማህበር በህጉ እና በመተዳሪያ ደንቡ መሰረት ኦዲት ተደርጎ የሚገኘውን ከ2009 ጀምሮ ለአባላቱ እኩል እንዲያካፍል እንዲወሰን ፣ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ከኃላፊነት እንዲነሱ እና ለወደፊትም ማህበሩን እንዳይመሩ እንዲወሰን፤ንግድ ሚኒስቴር የ1ኛ ተጠሪን ሀብት ኦዲት እንዲያደርግ፤መተዳደሪያ ደንቡና መመስረቻ ጽሁፉ እንዲሻሻል እንዲሁም የቦርድ እና የቁጥጥር ኮሚቴ ምርጫ እንዲካሄድ እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡

1ኛ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስ በንግድ ህግ ቁጥር 347(2) እና (3) መሰረት የአንድ ማህበር አስተዳዳሪዎች ብዛት ቢያንስ 3 ቢበዛ 12 ይሆናል በማለት መደንገጉን፤ የ1ኛ ተጠሪ አስተዳዳሪዎች በዚህ መካከል ያለ በመሆኑ ለህጉ ተቃራኒ አለመሆኑን፤1ኛ አመልካች ቀደም ሲል የማህበሩ የቦርድ

ሰብሳቢ ሆነው ሲሰሩ የቦርድ አባላትን 7 አድርገው ለ2 ጊዜ ያህል አስመርጠው ሲሰሩ የቆዩ መሆኑን፤ 1ኛ አመልካች በመጋቢት 02/2010 ዓ.ም በተደረገው የቦርድ አባለት ምርጫ የአባላቱ ብዛት 7 እንዲሆኑ በሰጡት ሀሳብ መሰረት ምርጫው መደረጉን፤ በዚህ ወቅት አመልካቾች ያቀረቡት ተቃውሞ ያለመኖሩን፤ ምርጫው የንግድ ሚኒስቴር እና የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት ተወካዮች በተገኙበት መደረጉን፤ 2ኛ ተጠሪ የቦርድ ሰብሳቢ እንጂ ዋና ስራ አስኪያጅ ባለመሆናቸው በተደራራቢ ስራ እና ሀላፊነት ላይ አለመሆናቸውን፤ ዋና ስራ አስኪያጅ ከአስተዳዳሪዎችም ሊመደብ የሚችል መሆኑን፤ተመርጠው አንሰራም ባሉት አባላት ምትክ በሀምሌ 2010 ዓ.ም በሚደረገው ጠቅላላ ጉባኤ የማሟያ ምርጫ የሚካሄድ መሆኑን በመግለጽ በመጋቢት 02 /2010 ዓ.ም የጸደቀው ቃለ ጉባኤ እንዲሰረዝ፤2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች እንዲነሱ የሚለው ክስ የህግ መሰረት የሌለው ነው፡፡ የማህበሩ የእለት ተእለት ስራዎች ማለትም የግዥና የጨረታ ውሎች ከቦርድ አባላት ጋር በስብሰባ በመወሰን የተሰሩ ስለመሆናቸው፤ማህበሩ እስከ 2008 ድረስ ያለውን ትርፍ ለማህበሩ ካፒታል ማሳደጊያ እንዲውል መወሰኑን፤ የ2009 ዓ.ም የትርፍ ክፍፍል መፈጸሙን፤ማህበሩ እያከራየ ያለውን ሱቆች ገቢ ለባለአክሲዮኖች እኩል እንዲከፋፈል የሚለው ጥያቄ ከጠቅላላ ጉባኤ ውጭ ስለሆነ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን፤የጠቅላላ ጉባኤ በወሰነው መሰረት ሱቆቹ በእጣ ለባለአክሲዮኖች መሰጠቱን፤የማህበሩን መመሰረቻ ጽሁፍ እና መተዳደሪያ ደንብ የንግድ ሚኒስቴር እንዲያሻሻል ያድርግ የተባለው ከህግ ውጭ መሆኑን፤የሚሻሻለው ምን እንደሆነም አለመግለጻቸውን፤ማህበሩ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ሂሳቡን በውጭ ኦዲተሮች ማስመርመሩን፤ሆኖም አመልካቾች በራሳቸው ወጪ ፈቃደኛ ከሆኑና ዋስትና ካስያዙ እንደገና ቢመረመር ማህበሩ ተቃውሞ እንደሌለው ገልጾ የቀረበው ክስ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቋል፡፡

2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በቀን 14/10/2010 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ በአክሲዮን አስተዳዳሪዎች ላይ የሚቀርበውን ክስ የሚወስነው የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ መሆኑንና፤ ጠቅላላ ጉባኤ ሳይወሰን አመልካቾች ክስ ማቅረብ እንደማይችሉ፤ጥፋት ስለመፈጸማቸው በጠቅላላ ጉባኤ የተሰጠ ውሳኔ ወይም ሪፖርት በሌለበት ሁኔታ አነስተኛ አክሲዮን ያላቸው አባላት ክስ ለማቅረብ የማይችሉ መሆኑን በመግለጽ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም ይህን መቃወሚያ በመቀበል 2ኛ እኛ 3ኛ ተጠሪዎች ከክርክሩ እንዲወጡ ያደረገ መሆኑን መዝገቡ ያስረዳል፡፡

ከዚህ በኋላም ፍ/ቤቱ የ1ኛ ተጠሪንና የአመልካቾችን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ በቀን 17/06/2012 ዓ.ም ውሳኔ የሰጠ ሲሆን በውሳኔም 1ኛ ተጠሪ በመጋቢት 02/2010 ባደረገው ጠቅላላ ጉባኤ የማህበሩ ቦርድ አባላት ምርጫና ምዝገባ አግባብነት ያለው እና ህጋዊ መሆኑን፤የማህበሩ ህንጻ ግንባታ ስራዎች በጨረታ እና በማስታወቂያ የተፈጸሙ እንደሆነ፤ከመመሪያ ውጭ ወጪ የተደረገ ገንዘብ አለመኖሩን፤የማህበሩ ሂሳብ በየአመቱ በውጭ ኦዲተር ሲመረመር እንደነበር፤የ2009 ዓ.ም ትርፍ

ክፍፍል መደረጉን ከግራ ቀኙ ምስክሮች መገንዘቡን በመግለጽ 1ኛ ተጠሪ ማህበር በመጋቢት 02/2010 ዓ.ም ያስተላለፈው የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ሊሰረዝ አይገባም፤ የ1ኛ ተጠሪ ማህበር ሂሳብ ኦዲት እየተደረገ ለጠቅላላ ጉባኤ እየቀረበ የነበረ በመሆኑ በድጋሚ ማህበሩ ኦዲት ሊደረግ አይገባም ሲል ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡

በዚህ ውሳኔ ላይ የአሁን አመልካቾች ቅር ተሰኝተው ይግባኛቸውን ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት መልስ ሰጪዎች መልስ እንዲያቀርቡ ካደረገ በኋላ በቀን 30/06/2014 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ 1ኛ ተጠሪ በህዳር 15 ቀን 2011 ዓ.ም በተደረገ ድንገተኛ ጉባኤ ታህሳስ 14 ቀን 2011 ዓ.ም ተመዝግቦ በጸደቀው ቃለ ጉባኤ ማህበሩ በጉባኤው በተመረጡ 7 የቦርድ አባላት እየተዳደረ መሆኑን፤ እንዲሁም ማሟያ ምርጫ ተካሂዶ የቦርድ አባለት ቁጥር ተሟልቷል፡፡ ስለሆነም ይግባኝ ባዮች ይግባኝ ያቀረቡበት ምክንያት የቀረ ስለሆነ አቤቱታው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 280 እና 79/2/ መሰረት ውድቅ ይደረግልን ሲል ያቀረበው መቃወሚያ በመጋቢት 02/2010 ዓ.ም የጸደቀው የማህበሩ ቃለ ጉባኤ በሚመለከት መልስ ያልተገኘለት ጉዳይ በመሆኑ መቃወሚያው ተቀባይነት የለውም፡፡ 1ኛ ተጠሪ ማህበር በየካቲት 30/1994 ባደረገው ጠቅላላ ጉባኤ የቦርድ አባላት ቁጥር 12 እንዲሆን መወሰኑን፤ይህ ውሳኔ በመካከላቸው አስገዳጅነት ያለው እና ህግ ሆኖ የሚያገለግል እንደሆነ፤የስር ፍ/ቤት የቦርድ አባላትን ብዛት በተመለከተ በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ላይ በአስገዳጅነት የተቀመጠ አይደለም በማለት የደረሰበት መደምደሚያ ከመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 8 ውጪ የተረጎመው እንደሆነ ጠቅሶ ማህበሩ በመጋቢት 02 ቀን 2010 ዓ.ም ባደረገው የዳይሬክተሮች ቦርድ ምርጫ የቦርድ አባላትን ቁጥር ከ12 ወደ 7 ዝቅ በማድረግ ያደረገው የቦርድ አባላት ምርጫ ከመተዳደሪያ ደንቡ ውጭ ስለሆነ ሊሰረዝ ይገባል ብሏል፡፡ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችን በተመለከተ በንግድ ህግ ቁጥር 348/4/ መሰረት ዋና ስራ አስኪያጅ ከአስተዳዳሪዎች ሊመረጥ እንደሚቻል የሚደነግግ መሆኑን፤ ይግባኝ ባዮች የጥቅም ግጭት መኖሩን ያላስረዱ መሆኑን፤ የአክሲዮን ትርፍ ድርሻ ክፍፍልን በተመለከተም የ2009 ዓ.ም ትርፍ ክፍፍል መደረጉን፤ የሱቆች ክፍፍልም በጠቅላላ ጉባኤ የተወሰነ መሆኑን፤ እንዲሁም ይግባኝ ባዮች የቦርድ ሰብሳቢ እና የቦርድ አባል በመሆን በጊዜው ያልተቃወሙት መሆኑን በመግለጽ በዚህ ረገድ ያቀረቡትን ይግባኝ ውድቅ በማድረግ የስር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁን ሰበር ቅሬታ የቀረበውም በዚህ ውሳኔ ላይ ሲሆን አቤቱታውም በአጭሩ፡- የስር ፍ/ቤት 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ከንግድ ህጉና ከማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ውጭ ለጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ ባለመታዘዝ ያደረሱትን ጉዳት በተመለከተ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 145 እንዲቀርብላቸው የጠየቁትን ማስረጃዎች ሳያስቀርብና ምስክር ሳይሰማ ከክርክሩ ውጪ ያደረጋቸው መሆኑን፤ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪ ያለ ጨረታና ያለ ውድድር የተለያዩ የግንባታ ስራዎች ማካሄዳቸውን፤ከማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ውጭ ገንዘብ ወጭ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸምዓለማአ የገ ለግልም!

ማድረጋቸውን፤የዳይሬክተሮች ቦርድ ምርጫው ከመተዳደሪያ ደንቡ ውጭ መደረጉን፤ምርጫው ሁከትና ብጥብጥ የነበረበት መሆኑን፤አክሲዮን ማህበሩ በንግድ ህጉና በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት በጋራ እየሰሩ ለመጠቀም እንጂ ሱቅ ለእያንዳንዱ አባል ለመከፋፋል የሚል አላማ የሌለው መሆኑን እና ከአላማው ውጭ ሱቆች መከፋፈላቸውን፤የማህበሩ ሀብትና ንብረት ኦዲት ያለመደረጉን ጠቅሰው የስር ፍ/ቤቶች በሰውና በሰነድ ማስረጃ የተረጋገጠውን ጉዳይ የህግ መሰረት የለውም ሲሉ ውድቅ ማድረጋቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነና በ1ኛ ተጠሪ ማህበር በመጋቢት 02/2010 ዓ.ም በተደረገው ጠቅላላ ጉባኤ የጸደቀው ቃለ ጉባኤ የተሻረ በመሆኑ በስልጣን ላይ ያለው የዳይሬክተሮች ቦርድ እንዲነሳ እና በምትኩ አዲስ ቦርድ በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት 12 የቦርድ አባላት እንዲመረጡ እንዲደረግ፤ በስልጣን ላይ ያለው ቦርድ 50 በመቶ በታች ሆኖ ሲሰራ የቆየ በመሆኑ የሰራቸው ስራዎች በሙሉ እንዲሻሩ እና ሀላፊነቱን እንዲወስዱ እንዲሁም ዳግመኛ በአመራር ደረጃ እንዳይመረጡ እንዲታዘዝ፤አክሲዮን ማህበሩ ከተቋቋመበት አላማ ውጭ እየሰራ ስለሚገኝ ይህ ህገ ወጥ ድርጊት እንዲቆምና በጋራ የማህበሩ ስራ እንዲካሄድ እንዲታዘዝልን የሚል ነው፡፡

የስር ፍርድ ቤት ቃለ-ጉባዔው እንዲሰረዝ ወስኖ መሰረዙ የሚያስከትለውን ውጤትም ሆነ ስለ ቦርድ አባላትና የውጭ ኦዲተር ጥያቄን በተመለከተ በዝምታ ያለፈበትን አግባብ ለማጣራት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ከተባለ በኋላ ተጠሪዎች በጋራ በቀን 24/05/2015 በተጻፈ በሰጡት መልስ የአመልካቾች አቤቱታ በመሠረታዊ የሕግ ስህተት ምክንያት ለሰበር ሰሚ ችሎት የሚቀርብ ሳይሆን የፍሬ ነገር ሐተታና በማስረጃ ምዘና ላይ ያተኮረ መሆኑን፣ የስር ፍ/ቤት የግራ ቀኛቸውን ምስክሮች መስማቱን፤ የራሳቸው ምስክሮች ክሳቸውን ውድቅ የሚያደርግ የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተው እያለና መሰማታቸውንም ራሳቸው እያረጋገጡ ምስክሮቻችን ሳይሰሙ ተወሰነብን የሚል እርስ በርሱ የሚቃረን አቤቱታ ያቀረቡ መሆኑን፣ለከፍተኛው ፍ/ቤት ባቀረቡት የይግባኝ አቤቱታ በ145 መሠረት የጠየቁት ማስረጃ ሳይቀርብ ስለመታለፉ ሳይጠይቁና ሳይጠቅሱ በሰበር አቤቱታ ላይ አዲስ ያቀረቡት ጥያቄ መሆኑን፣ በህዳር 15 ቀን 2011 ዓ.ም  በማህበሩ ድንገተኛ ጉባዔ ስብሰባ ውሳኔ እና ታህሳስ 4 ቀን 2011 ዓ.ም ተመዝግቦ በጸደቀው ቃለ ጉባዔ በተሻሻለው ደንብ መሠረት ማህበሩ በጉባዔው በተመረጡ 7 የቦርድ አባላት ብቻ የሚተዳደር መሆኑን፤በንግድ ሕጉና በተሻሻለው የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት የማሟያ ምርጫዎች መካሄዳቸውን፤የማህበሩ ዋና እና ምክትል ሥራ አሥኪያጆችም ለቦርዱ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት በቅጥር መመደባቸውን፤በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 280 ላይ ክሱ በሚቀጥልበት በማንኛውም ጊዜ ለክሱ ምክንያት የሆነው ነገር መቋረጡን ወይም ጨርሶ መቅረቱን ፍ/ቤቱ በቂ በሆነ ማስረጃ የተገነዘበ እንደሆነ ክሱን /መዝገቡን ይዘጋዋል በማለት የተደነገገ በመሆኑ አመልካቾች የቃለ ጉባዔውን መሠረዝና የሚያስከትለውን ውጤት እንዲሁም የቦርድ አባላትን ምርጫ በተመለከተ ያቀረቡት አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ የሚገባ መሆኑን፤በሥር ፍ/ቤት የቀረቡ የግራ ቀኙ ምስክሮችና የሰነድ ማስረጃዎች በመጋቢት 02/2010 ዓ.ም የተደረገውን የዳይሬክተሮች ቦርድ እና የቁጥጥር ኮሚቴ

አባላት ምርጫ 1ኛ አመልካች በሰብሳቢነት ማስመረጣቸውንና አንድ ከሳሽ በራሱ ሰብሳቢነት ያስወሰነውን፣ያስመረጠውንና ሲሠራበት የቆየውን የራሱን ሥራ መከራከሪያ ሊያደርግ አይገባውም የሚለውን መርህ የሚጥስ መሆኑን፤በን/ህ/ቁ 347(2) እና (3) መሠረት የአንድ አክሲዮን ማህበር አስተዳዳሪዎች ብዛት ቢያንስ 3 ቢበዛ 12 መሆን እንዳለበትና ማህበሩ ከፍተኛ እና አነስተኛ የቦርድ አባል ቁጥር ብቻ ያስቀመጠ እንደሆነ ከዚህ መካከል ያለ የቦርድ አባላት ቁጥር በማህበረተኞች ሊወሰን እንደሚችል የሚደነግግ መሆኑን፤የውጭ ኦዲተርን በተመለከተ በየዓመቱ የውጭ ኦዲተር ሪፖርት እየቀረበና በጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔዎች እየጸደቀ የሚሠራ መሆኑን፤ ማህበሩ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 2014 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ በየዓመቱ በውጪ ኦዲተሮች ሂሣቡን ማስመርመሩን፤ከሣሾች በራሳቸው ወጪ ሂሣቡን ለማስመርመር ፈቃደኛ ከሆኑና ዋስትና ካስያዙ የማህበሩ ሂሣብ የየዓመቱ እንደገና ቢመረመር ማህበሩ ተቃውሞ የሌለው መሆኑን፤2ኛ ተጠሪ በአሁኑ ጊዜ የማህበሩ ሥራ አስኪያጅ አለመሆናቸውን፤ 3ኛ ተጠሪም በአሁኑ ጊዜ በማህበሩ ውስጥ የቦርድ አባል እንጂ ም/ዋና ስራ አስኪያጅ አለመሆናቸውን፤ የጥቅም ግጭት እና የተፈጠረ ጉዳት ደርሷል በማለት የቀረበው አቤቱታ የደረሰ የጥቅም ግጭት ስለመከሰቱ አንዳች ማስረጃ ሳይኖር የቀረበ የፍሬ ነገር እና የሕግ መሠረት የሌለው ስለመሆኑ፤ የማህበሩ የትርፍ ክፍፍል በማህበሩ ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ መሠረት የሚከናወን በመሆኑ ያለ ተቃውሞ በጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ መሠረት የማህበሩን አባላት ጥቅማና ፍላጎት መሠረት ባደረገ የትርፍ ክፍፍል አሠራርና ዓይነት መደረጉን፤የማህበሩ ስራዎችም በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት መከናወናቸውን በመግለጽ የአመልካቾች አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቀዋል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለመልኩ የተገለጸዉ የግራ ቀኙ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት የሚመለከት ሲሆን እኛም የማስቀረቢያውን ጭብጥ መሰረት በማድረግ  በውሳኔው ላይ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡አንድ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ተከራካሪ ወገኖች ክርክር መሰረት አድርጎ ተገቢውን ፍርድ የሚሰጠው ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ክስ መሰረት በማድረግ ሲሆን በዚህ አግባብም ፍርድ ቤቱ ባላጉዳዮቹን ማከራከር የሚገባው የተለያዩበት የህግ ወይም የፍሬ ነገር አግባብ ምን እንደሆነ አረጋግጠ ለጉዳዩ ትክክለኛ ጭብጥ በመያዝ ስለመሆኑ፤የነገር ጭብጥ የሚመሰረተው አንደኛው ተከራካሪ ወገን ያመነውን የህግ ወይም የነገር አግባብ ሌላኛው ተከራካሪ ወገን በማስተባበል የካደ በሆነ ጊዜ ስለመሆኑ፤ፍርድ ቤቱ ጭብጥን ለመመስረት የሚችለውም ከግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እና ማስረጃ እንዲሁም በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.241 መሰረት በሚደረግ ምርመራ በተከራካሪ ወገኖች  የሚሰጠውን መልስ መሰረት በማድረግ ስለመሆኑ የጭብጥ አመሰራረትን በሚደነግጉት ከቁጥር 246 እስከ 248 በተመለከቱት ድንጋጌዎች የተመለከተ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ውሳኔ በሚሰጥበትጊዜ በክርክሩ የተያዘው ጭብጥ ምን እንደሆነ እና ጭብጡ በአንድ ወይም በሌላ አግባብ የተወሰነበትን ምክንያት በውሳኔው ላይ መግለፅ ያለበት ስለመሆኑ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.182(2) በአስገዳጅነት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርዶ አፈጸጸምዓለማአ የገለግልም!

ተደንግጎ ይገኛል፡፡ (በሰ/መ/ቁ.105869፤239141 እና በተመሳሳይ መዝገቦች የተሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም ይመለከቷል፡፡)

አሁን በያዝነው ጉዳይ አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት መጋቢት 14 ቀን 2010 ዓም ከተያዘው ቃለ-ጉባዔ ጋር በተያያዘ ክሳቸውን ያቀረቡት ከማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ውጪ ሰባት የቦርድ አባላት ብቻ እንዲመረጡ መደረጉን፤ከነዚህ የቦርድ አባላት መካከልም ሶስቱ የቦርድ አባል ሆነው መስራት እንደማይፈልጉ ገልፀው እያለ፤አስመራጭ ኮሚቴውም የልዩነት ሀሳብ እንዳለው እየታወቀ ቃለ-ጉባዔው ለሰነዶች ምዝገባ እና ማረጋገጫ ኤጀንሲ ሳይቀርብ አራቱ ተመራጮች የቦርድ አባላት ነን ብለው ከህግ ውጪ ማስመዝገባቸውን በመቀወስ ቃለ-ጉባዔው እንዲሰረዝና ውድቅ እንዲሆን ይህንን ተከትሎም የቦርድና የቁጥጥር ኮሚቴ ምርጫ እንዲካሄድ በመጠየቅ ነው፡፡የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የቦርድ አባላቱ ምርጫ በህጉ አግባብ የተከናወነ መሆኑን በመቀወስ አመልካቾች ያቀረቡትን ክስ ውድቅ በማድረግ የወሰነ ቢሆንም ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት 1ኛ ተጠሪ ማህበር በየካቲት 30/1994 ባደረገው ጠቅላላ ጉባኤ የቦርድ አባላት ቁጥር 12 እንዲሆን መወሰኑን፤ይህ ውሳኔ በመካከላቸው አስገዳጅነት ያለው እና ህግ ሆኖ የሚያገለግል እንደሆነ፤የስር ፍ/ቤት የቦርድ አባላትን ብዛት በተመለከተ በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ላይ በአስገዳጅነት የተቀመጠ አይደለም በማለት የደረሰበት መደምደሚያ ከመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 8 ውጪ የተረጎመው እንደሆነ ጠቅሶ ማህበሩ በመጋቢት 02 ቀን 2010 ዓ.ም ባደረገው የዳይሬክተሮች ቦርድ ምርጫ የቦርድ አባላትን ቁጥር ከ12 ወደ 7 ዝቅ በማድረግ ያደረገው የቦርድ አባላት ምርጫ ከመተዳደሪያ ደንቡ ውጭ ስለሆነ ሊሰረዝ ይገባል በማለት መወሰኑን ይህ ውሳኔም በየደረጃው ባሉት ፍርድ ቤቶች መፅናቱን መዝገቡ ያሳያል፡፡

የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከላይ እንደተመለከተው የቦርድ አባላቱን ቁጥር ከ12 ወደ 7 ዝቅ በማድረግ የተከናወነው የቦርድ አባላት ምርጫ የማህበሩን መተዳደሪያ በሚፃረር መልኩ የተፈፀመ በመሆኑ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ሲወስን የቦርድና የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት ምርጫ እንዲካሄድ በመጠየቅ በአመልካቾች ከቀረበው የዳኝነት ጥያቄ አንፃር ተገቢውን ውሳኔ ሊያሳልፍ ሲገባ በዝምታ ማለፉ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.182(2) አግባብ ለተጠየቀው ዳኝነት ተገቢውን እልባት አለመስጠቱትን በዚህ አግባብም ከክርክር አመራር አንፃር መሰረታዊ የህግ ስህተት መፈፀሙን ያሳያል፡፡ከዚህ ባለፈ ግን አመልካቾች ከላይ እንደተመለከተው በክሳቸው ከመነሻውም በስልጣን ላይ ያለው ቦርድ 50 በመቶ በታች ሆኖ ሲሰራ የቆየ በመሆኑ የሰራቸው ስራዎች በሙሉ እንዲሻሩ በማለት በስር ፍርድ ቤት ክሳቸውን ሲያቀርቡ ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ በሌለበት በዚሁ የዳኝነት ነጥብ ላይ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ተገቢውን ፍርድ አላሳረፈም የሚባልበት አግባብ ባለመኖሩ በዚህ ረገድ አመልካቾች ያቀረቡትን የሰበር ቅሬታ አልተቀበልነውም፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

ከሌሎች የማስቀረቢያ ነጥቦች አንፃር የግራ ቀኙን የሰበር ክርክር ስንመረምረውም የማህበሩ ሀብትና ንብረት ኦዲት ያለመደረጉን ጠቅሰው የስር ፍ/ቤቶች በሰውና በሰነድ ማስረጃ የተረጋገጠውን ጉዳይ የህግ መሰረት የለውም ሲሉ ውድቅ ማድረጋቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት የሰበር ቅሬታ ማቅረባቸውን መዝገቡ ያሳያል፡፡በመሰረቱ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 80(3)(ሀ) እና በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 2(4) እና 10(1) እንደተመለከተው ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው የዳኝነት ስልጣን በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞ ሲገኝ በሰበር አይቶ የማረም ነው፡፡በአዋጁ በትርጉም ክፍል አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለዉ አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን፣ ህግ ያላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉን ህግ የሚጠቅስ፣ ለክርክሩ አግባብነት ያለዉ ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለዉ ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፣ በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ዉድቅ በማድረግ የተወሰነ፣ በፍርድ አፈፃፀም ሂደት ከዋናዉ ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትዕዛዝ የተሰጠበት፣ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተወሰነ፣ የአስተዳደር አካል ወይም ተቋም ከህግ ዉጭ የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ በመቃረን የተወሰነ ሲሆን ነዉ፡፡በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በሚል የሰበር አቤቱታ ሲቀርብለት ለአቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ ጉዳይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ ከላይ በዝርዝር ከተመለከቱት ሁኔታዎች ዉስጥ ቢያንስ አንዱን ያሟላ ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 10 ላይ ከተመለከቱት ድጋጌዎች የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡ በዚህ አግባብም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር ሰሚነት ስልጣኑን ተግባራዊ ሲያደርግ ፍሬ ነገርን በተመለከተ በዋነኝነት መነሻ የሚያደርገው ስልጣን ባላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች ነው፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይ ማስረጃዎችን የመስማት፤ የመመርመር እና የመመዘን በህግ ስልጣን የተሰጠው የስር የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በግራቀኙ የቀረቡትን ምስክሮች በመስማትና እና በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.145 መሰረት ትእዛዝ ያስቀረባቸውን ማስረጃዎች በመመርመር የማህበሩ ሂሳብ በየአመቱ በባለሙያ ኦዲት ተደርጎ ሪፖርት ሲቀርብ የነበረ መሆኑን ማረጋገጡን በውሳኔው ላይ አመልክቷል፡፡ይህንኑ ውሳኔ ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ከመነሻውም ናሙና ተወስዶም ቢሆን ኦዲት መሰራቱን በመጥቀስ አመልካቾች የይግባኝ ቅሬታቸውን ማቅረባቸውን መነሻ በማድረግ ሌሎች የማስቀረቢያ ነጥቦችን ሲዘረዝር ይህንኑ ነጥብ የማስቀረቢያ ነጥብ አድርጎ አለመጥቀሱ  ማስረጃን የመስማት/የመመርመርና የመመዘን ስልጣኑን ተጠቅሞ በዚህ ረገድ የቀረበውን የይግባኝ ቅሬታ አልተቀበለውም ከሚባል በስተቀር ለአመልካቾች የይግባኝ ቅሬታ ተገቢውን እልባት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አረጻጸምዓለማአ የገ ለግልም!

አልሰጠም የሚባልበት አግባብ አይኖርም፡፡በአጠቃላይ የስር ፍርድ ቤቶች የግራ ቀኙን ማስረጃዎች በመስማት፤በመመርመርና በመመዘን በዚህ ረገድ የደረሱበት ድምዳሜ ተገቢውን ማጣራት በማድረግ ለጉዳዩ ተገቢውን እልባት መስጠታቸውን ከሚያሳይ በስተቀር በፌደራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4) እና አንቀጽ 10(1) ከተደነገገው አንፃር መሰረታዊ የህግ ስህተት መፈፀማቸውን የሚያሳዩ ሆነው ስላልተገኙ፤የሱቅ ክፍፍልን በተመለከተም ክፍፍሉ የተፈፀመው ህዳር 15 ቀን 2011 ዓም የማህበሩ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ አግባብ መሆኑን በዕለቱ የተያዘው ቃለ-ጉባዔ እያሳየ፤አመልካቾች ተገቢውን የዳኝነት ጥያቄ በማቅረብ ይህንን ቃለ-ጉባዔ የህግ ውጤት እንዲያጣ ባላደረጉበት ፀንቶ ባለው ቃለ-ጉባዔ አግባብ የተፈፀመው ክፍፍል የህግ ውጤት ሊያገኝ አይገባም በማለት መከራከራቸው አግባብነት ያለው ሆኖ ባለመገኘቱ፤በአጠቃላይ ከነዚህ የሰበር ቅሬታ ነጥቦች አንፃር የስር ፍርድ ቤቶች የፈፀሙት መሰረታዊ የሕግ ስህተት ባለመኖሩ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ውሳኔ</u>

1.የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 258937 በቀን 30/06/2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስነስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9(1)(ለ) መሰረት ተሻሽሏል፡፡

1.1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከሱቅ ክፍፍል እና ከማህበሩ ኦዲት ጋር በተያያዘ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የደረሰበትን መደምደሚያ በመቀበል የሰጠው የውሳኔ ክፍል ከውጤት አንፃር ፀንቷል፡፡

1.2. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቦርድ አባላቱን ቁጥር ከ12 ወደ 7 ዝቅ በማድረግ የተከናወነው የቦርድ አባላት ምርጫ የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ በሚፃረር መልኩ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓለማአየገለግልም!

የተፈፀመ በመሆኑ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ሲወስን የቦርድና የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት ምርጫ እንዲካሄድ በመጠየቅ በአመልካቾች ከቀረበው የዳኝነት ጥያቄ አንፃር ተገቢውን ውሳኔ ሳያሳልፍ ማለፉ አግባብ አይደለም ብለናል፡፡

2. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የጉዳዩን መዝገብ በማንቀሳቀስ የአክሲዮን ማህበሩ የቦርድና የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት ምርጫ እንዲካሄድ በመጠየቅ አመልካቾች ባቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ላይ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስነስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9(2) መሰረት ተመልሶለታል፡፡

3.የስር ፍርድ ቤት መዝገብ በመጣበት አኳኋን ይመለስ፡፡

4.ግራ ቀኙ በሰበር ክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

**<u>ጉዳዩ ውሳኔ ስላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡</u>**

____የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ም

## <u>የሃሳብ ልዩነት</u>

ስሜ በተራ ቁጥር አምስት ላይ የተሰየምኩት ዳኛ በአብላጫው ሃሳብ የቦርድና ቁጥጥር አባላት ምርጫ እንዲደረግ የተሰጠው ውሳኔ የምስማማበት ቢሆንም በሌሎች የውሳኔ ክፍሉ ላይ የተለየሁበትን ምክንያት እንደሚከተለው አስፍሬያለሁ፡፡

ክርክሩን በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሰረት መምራት እና መቆጣጠር የፍርድ ቤቱ ኃላፊነት ሲሆን በተገቢው ሁኔታ ካልተመራ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ዓላማዎች የሆኑትን እንደ አንጻራዊ እውነትን የመፈለግ፣ ሥነ-ሥርዓታዊ ፍትህ፣ ክርክርን ውጤታማ፣ ወጭና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ መምራት

የመሳሰሉትን ማሳካት ስለማይቻል የተከራካሪዎችን መብት ይነካል፡፡ ክርክር የሚወሰነው በተጠየቀው ዳኝነት አግባብ እንደሆነ የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 182(2) ላይ ተመልክቷል፡፡ ፍርድ ቤቱም ከቀረበው ዳኝነት አኳያ ከግራቀኙ ክርክር በመነሳት በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 246 እና ተከታዮቹ መሠረት በተነሱት ጉዳዮች ጭብጥ መስርቶ ውሳኔ የመስጠት ኃላፊነት አለበት፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች በሥር ፍርድ ቤት ካቀረቡት ዳኝነት አንዱ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ካላቸው የሥራ-አስኪጅነትና የቦርድ አባልነት ድርብ ኃላፊነት እንዲሱ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቦርድ አባላት ምርጫ የተደረገበትን ቃለ-ጉባዔ የሰረዘ በመሆኑ በውጤቱ ከቦርድ ኃላፊነት ተነስተዋል፤ በሌላ በኩል 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ከሥራ-አስኪያጅነት ሊያስነሳ የሚያስችል ጥፋት ፈጽመዋል ወይስ አልፈጸሙም የሚለው ጭብጥ ተይዞ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ባሉበት ክርክርና ማስረጃ ከሥራ አስኪያጅነት መነሳት አለመነሳታቸው ላይ በሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊሰጥበት ሲገባ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አስቀድሞ ከክርከሩ ውጭ ያደረጋቸው በመሆኑ በተገቢው ሁኔታ ውሳኔ ያልተሰጠበት መሆኑ መሠረታዊ የሆነ የክርክር አመራር ግድፈት ስለሆነ ታርሞ በዚህ ነጥብ ላይ ክርክር ተደርጎ እንዲወሰን ጉዳዩ ሊመለስ ይገባል፡፡

1ኛ ተጠሪ አክሲዮን ማሕበር በመሆን በነጋዴነት የሚሰራ ማሕበር ነው፣ በአክሲዮን ማሕበሩ የተገነባው ሕንጻ ለባለአክሲዮኖች ከተከፋፈለ ማሕበሩ ነጋዴ ሆኖ ሊቀጥል አይችልም፣ ተግባሩ መሆን ያለበት የንግድ ሕንጻ ከተገነባ የሚገኘውን ገቢ እየሰበሰበ ለባለአክሲዮኖች ባላቸው የአክሲዮን ድርሻ ልክ ትርፉን ማከፋፈል ነው፡፡ በዚህ ረገድም የንግድ ሚኒስቴር የንግድ ሕንጻውን አከራይቶ ባለአክሲዮኖች ትርፉን እንዲያከፋፍል ውሳኔ መስጠቱን ከክርክሩ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በሕዳር 15 ቀን 2011 ዓ/ም በተደረገው ቃለ-ጉባዔ ሕንጻው ላይ የሚገኙ ሱቆች ክፍፍል ተደርጎባቸዋል ወይስ እንዲከራዩ ተደርጓል፣ 1ኛ ተጠሪ ኪራይ እየሰበሰበ ትርፍ የማከፋፈል ተግባር እየፈጸመ ነው ወይስ ለባለአክሲዮኖች ሱቁን አከፋፍሏል የሚለው በአግባቡ ሳይጣራ የተሰጠው ውሳኔ ባለአክሲዮኖች ባላቸው አክሲዮን ልክ እኩል የመጠቀም መብትን የሚጥስ በመሆኑ ክርክሩ በሥርዓት ተመርቶ እንዲወሰን በሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/2/ መሠረት ጉዳዩ ሊመለስ ይገባ ነበር በማለት በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ብ/ም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸምዓለማአ የገለግልም!

የሰ.መ.ቁ.233458

ጥቅምት 06 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች፡......1. ብርሃኑ አመነዉ

2. በእዉቀት በላይ

3. ቀነዓ ቂጣታ

4. ብርሃኑ መንግስቱ

5. ማርታ ተካ

አመልካች፡ ........አቶ ዘዉዱ ነጋሽ -የቀረበ የለም

ተጠሪ፡............... የኦሮሚያ ክልል ዐቃቤ ሕግ-ዐ/ሕግ ግርማ ሙሉጌታ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ይህ የሕገወጥ ንግድ ወንጀል ክርክር የተጀመረዉ በግራር ጃርሶ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች የሥር ተከሳሽ፣ የአሁን ተጠሪ የሥር ከሳሽ ሆኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ ይህ ጉዳይ ለዚህ ሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.404705 በ15/10/2014 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ ከሳሽ በሥር ፍ/ቤት ባቀረበዉ የክስ አቤቱታ፡ ተከሳሽ 1ኛ በፍቼ ከተማ አስተዳደር 04 ቀበሌ ልዩ ስሙ ኮማንዶ ተብሎ በሚጠራዉ አካባቢ የሥጋ ቤት የንግድ ሥራ ለመስራት ፈቃድ አዉጥቶ ሲሰራ በነበረ ጊዜ የ2010 ዓ.ም የንግድ ትርፍ ግብር፣ ዋና ግብር፣ ቅጣትና ወለድ በአጠቃላይ ብር 204527.84፣ የ2011 ዓ.ም የንግድ ትርፍ ግብር፣ ዋና ግብር፣ ወለድና ቅጣት በአጠቃላይ ብር 334672.33 ተከሳሽ ይህን ግብር እንዲከፍል ማስታወቂያ

ማሳሰቢያ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የተሰጠዉ ቢሆንም ሳይከፍል የቀረ በመሆኑ የሚፈለግበትን ግብር ባለመክፈል ወንጀል ተከሷል፣ እና 2ኛ ተከሳሽ በተጠቀሰዉ ንግድ ፈቃድ የ2010 ዓ.ም የተጨማሪ እሴት ታክስ ላለመልፈል በማሰብ ሆነ ብሎ ብር 46643.15 እና የ2011 ዓ.ም የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 147936.70 ለመንግስት ሳይከፍል የቀረ በመሆኑ በፈጸመዉ የተጨማሪ እሴት ታክስ ባለመክፈል ወንጀል ተከሷል፣ እና 3ኛ ተከሳሽ አስቦበት በ1ኛ እና 2ኛ ክሶች በተጠቀሰዉ ጊዜ እና የንግድ ፈቃድ ለሥጋ ቤት ንግድ ሥራ ተመዝግቦ ሲሰራ የነበረ ሲሆን ተከሳሽ በየዓመቱ የንግድ ፈቃድ ማደስ ሲገባዉ ይህን ሳያደርግ ከሐምሌ 30 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ታህሳስ 30 ቀን 2011 ዓ.ም የንግድ ፈቃዱን ሳያድስ ሲሰራ የቆየ በመሆኑ ሕገወጥ ንግድ በመሥራት ወንጀል ተከሷል የሚል ነዉ፡፡

ተከሳሽ ፍ/ቤት ቀርቦ ክሱ ተነበለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን ያነሳቸዉ ቢሆንም ፍ/ቤቱ መቃወሚያዎቹን በብይን ዉድቅ በማድረጉ፣ ተከሳሽ በሰጠዉ የእምነት ክህደት ቃል 1ኛ ክስ በተመለከተ እኔ የንግድ ትርፍ ግብር አልከፍልም አላልኩም ግብሩ ከአቅሜ ላይ ስለሆነ መክፈል አልችልም እንዲታይልኝ በማለት ተለያየ ጊዜ ለገቢዎች ባለስልጣን ጽ/ቤት አቅርቤአለሁ፣ 2ኛ ክስ የተጨማሪ እሴት ግብር ለመክፈል እምቢ አላልኩኝም ነገር ግን ካንተ የሚፈለገዉ ይህ ብቻ አይደለም ብለዉኝ እምቢ ስላሉኝ መክፈል አልቻልኩም፣ ተከሳሽ ግብሩ በመብዛቱ ምክንያት እና የንግድ ትርፍ ግብር ስላልከፈልሉኝ የንግድ ፈቃድ ማደስ አልቻልኩም፣ ግብር ከተከፈለ እንጂ የንግድ ፈቃድ ስለማይታደስ ነዉ በማለት ሰጥቷል፡፡ በመቀጠል ዐቃቤ ሕግ የሰዉ ምስክሮችን በመስማትና የሰነድ ማስረጃ በመመርመር ተከሳሽ የተከሰሰበትን ወንጀል እንደዐቃቤ ሕግ ክስ ስለመፈጸሙ በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ስለተነገረበት የቀረበበትን ክስ እንዲከላከል በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ በዚህ መሰረት ተከሳሽ የመከላከያ የሰዉ ምስክሮችን በማቅረብ ያሰማ ሲሆን ተከሳሽ የሥጋ ቤት ንግድ ፈቃድ አዉጥቶ ሲሰራ የነበረ መሆኑን፣ ከአቅሜ ላይ ግብር ተጨምሮብኛል፣ ግብርና ቫት አብዝተዉብኛል፣ ግብሩ በገብዬ ልክ ከተሰራ እከፍላለሁኝ እየለ እንደነበር መስክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ የሥር የወረዳዉ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ በመመዘንና በመመርመር በሰጠዉ ዉሳኔ ተከሳሽ በዐቃቤ ሕግ የቀረበበትን ክስና ማስረጃ ባቀረበዉ የመከላከያ ማስረጃ ያልተካተለ በመሆኑ በተከሰሰበት በሶስቱም ክሶት በኦሮሚያ ክልል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 203/2009 አንቀጽ 125 (1)፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 75/1995 አንቀጽ 26 እና የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 49 (2) ሥር የጥፋተኝነት ዉሳኔ በመስጠት፣ የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት በመቀበል ቅጣቱ በፌዴራሉ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሰረት በመመርመር ተከሳሽ በ11 ዓመት ጽኑ እስራት እና በብር 126000 የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ የቅጣት ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡ ተከሳሽ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን በማከራከር የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በአብላጫ ድምጽ በማጽናት ወስኗል፡፡ ተከሳሽ አሁንም በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ ተከሳሽ የሚፈለግበትን የግብር እዳ አስቦበት አለመክፈሉ እና የገቢዎች ባለስልጣን ጽ/ቤት የግብር እዳዉን ለማስከፈል የተከሳሽን ንብረት ይዞበት እንዳያስከፍል ንብረቱን መደበቁና ማሸሹ ባልተረጋገጠበት በ1ኛ ክስ የኦሮሚያ ክልል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 203/2009 አንቀጽ 125 (1) እና በ2ኛ ክስ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 75/1995 አንቀጽ 26 ሥር የጥፋተኝነት እና የቅጣት ዉሳኔ

መስጠቱ ተገቢ አይደለም በማለት በመሻር፣ 3ኛ ክስን የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 49 (2) በመተላለፍ ሕገወጥ ንግድ መስራት በሚል የቀረበዉን በተመለከተ ምንም ሳይል ግን ደግሞ በዚህ ረገድ የሥር ፍ/ቤት የሰጠዉን የጥፋተኝነት ዉሳኔ የተቀበለ በሚመስል ሁኔታ ተከሳሽ በ5 አመት ጽኑ እስራትና በብር 20000 የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ መወሰኑን የዉሳኔዉ ግልባጭ ያሳያል፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበለትን የሰበር አቤቱታዉ ዉድቅ በማድረግ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤተታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች በ19/12/2014 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ አመልካች የሥጋ ቤት ንግድ ሥራ ፈቃድ ሳይኖረዉ ሰርቷል የተባለዉ ከሐምሌ 30 ቀን 2010 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 30 ቀን 2011 ዓ.ም ባለዉ ጊዜ ፈቃድ ሳላድስ በነበረኝ ፈቃድ መስራት የሚችልበት ሆኖ ሳለ የተሰጠዉ የጥፋተኝነት እና የቅጣት ዉሳኔ የህግ ስህተት የተፈጸመበትና ሊታረም የሚገባዉ ነዉ፤ ስለዚህ ዐቃቤ ሕግ ባቀረበዉ 3ኛ ክስ ጊዜ ዉስጥ በነበረኝ ባልታደሰዉ የንግድ ፈቃድ የንግድ ሥራዉን የሰራሁበት ቢሆንም በዚህ ጊዜ ዉስጥ ግን በነበረኝ የንግድ ፈቃድ መስራት የሚችልበት ጊዜ ነዉ፤ በ1ኛ እና 2ኛ የዐቃቤ ሕግ ክሶች ላይ የተጠቀሰዉ የታክስ ክፍያ ከንግድ ሥራዬ ከማገኘዉ ትፍር ጋር የማይመጣጠንና በኦድት አገኘነዉ ያሉትን የገንዘብ መጠን መክፈል ባለመቻል እና የንግድ ፈቃዱ ደግሞ ሊታደስ የሚችለዉ ግብር አስከፋዩ መ/ቤት ለንግድ ቢሮ የተጠየቀዉን የግብር መጠን መክፈልን የሚያሳይ ክሊራንስ ካልተጻፈልኝ ፈቃዱን ሳያድስልኝ የቆየ መሆኑን ከግራ ቀኙ ክርክር የሚታይ ስለሆነ አመልካች በወ/ሕ/ቁ.23 ሥር በተደነገገዉ መሰረት ወንጀል ለመፈጸም ሃሳብ ኖሮኝ ድርጊቱን ያልፈጸምኩ ሆኖ እያለ የሥር ፍ/ቤቶች በ3ኛ ክስ ሥር የጥፋተኝነት እና የቅጣት ዉሳኔ መወሰናቸዉ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ዉሳኔዉ ተሽሮ በነጻ እንዲሰናበት በማለት አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት የሰበር አቤቱታዉን በማየት ፣በአመልካች ላይ የቀረበበት 3ኛ ክስ ከሐምሌ 30 ቀን 2010 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 30 ቀን 2011 ዓ.ም የንግድ ፈቃድ ሳያሳድስ ነግዷል በሚል በመሆኑ በንግድ ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 686/2002 መሰረት የበጀት አመቱ ከሐምሌ 1 እስከ ታህሳስ ቀን ድረስ ያለቅጣት የሚታደስ መሆኑ ለአመልካች በተሰጠዉ የንግድ ፈቃድ ግርጌ ላይ በተጻፈበት ሁኔታ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች ፈቃድ ሳያሳድስ ሰርቷል በሚል ይህ ግምት ሳይገባ የጥፋተኝነት እና የቅጣት ዉሳኔ የሰጡበትን አግባብነት፣ መመርመር ሲባል የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባ በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ባዘዘዉ በ22/5/2015 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት ባጭሩ፡ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 49 ሥር የተከሰሰዉ ጥፋተኛ የተባለዉና የተቀጣዉ ከሐምሌ 30 ቀን 2010 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 30 ቀን 2011 ዓ.ም ጊዜ ዉስጥ በመስራቱ ሳይሆን ፈቃዱን ለማሳደስ በሕጉ ከተሰጠ ጊዜ በኂላም የንግድ ሥራዉን መስራቱን በሰዉ ምስክርና በሰነድ ማስረጃ እንደክሱ ያስረዳን ስለሆነ አመልካች ባቀረበዉ የመከላከያ ምስክር ማስተባበል በለመቻሉ የተሰጠዉ ዉሳኔ ስህተት የሌለዉ በመሆኑ እንዲጸናልን በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች በ30/5/2015 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ ይህ ሰበር ችሎት በያዘዉ ተጨማሪ ጭብጥ ፤በአመልካች ላይ የቀረበዉ የ3ኛ ክስ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 49 (2)ን ተላልፏል የሚል ሆኖ አንቀጹን መተላለፍ ደግሞ እስከ 15 አመት ድረስ በሚደርስ በጽኑ እስራት ስለሚያስቀጣ ክሱ የቀረበለት ግራር ጃርሶ ወረዳ ፍ/ቤት ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣን ለማየት ስልጣን ያለዉ መሆን አለመሆኑን በኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 50 (8)፣ 52 (2) (ለ)፣ 55 (5)፣ በተሻሻለዉ የኦሮሚያ ክልል ሕገ መንግስት አዋጅ ቁጥር 46/1996 አንቀጽ 49 (3)፣ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነሥርዓት ሕግ አንደኛ ሰንጠረዥ በተመለከተ ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር እንዲያቀርቡ አዟል፡፡ በዚህ መሰረት ተጠሪ በ7/1/2016 ዓ.ም በተጻፈ የጽሑፍ ክርክር በኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 78 (3) መሰረት የክልል ፍ/ቤቶች የተቋቋሙ በመሆኑ፣ አዋጅ ቁጥር 980/2008 የንግድ ምዝገባና ፈቃድ የሚነሱ ክርክሮችን በግልጽ የክልል ፍ/ቤቶች ማየት አይችሉም የሚል ድንጋጌ ያላስቀመጠ በመሆኑ ይህ ጉዳይ በክልል የወረዳ ፍ/ቤት መታየቱ ስህተት አይደለም፤ አመልካች የንግድ ፈቃዱን ያገኘዉ ከኦሮሚያ ክልል ሲሆን የንግድ ተግባሩንም እያካሄደ ያለዉ በዚሁ ክል በመሆኑ የወረዳዉ ፍ/ቤትን ይህን ጉዳይ ማየቱ ስህተት የለዉም፤ አመልካች የዉጭ ዜጋ ባለመሆኑ ጉዳዩ በክል የወረዳ ፍ/ቤት መታየቱ ስህተት የለዉም፣ በኦሮሚያ ክልል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 216/2011 አንቀጽ 31 (3) እስከ 15 ዓመት ሊደርስ የሚችል ጽኑ እስራት የሚያስቀጡ የወንጀል ጉዳዮችን የወረዳዉ ፍ/ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ለማየት ስልጣን እንዳላቸዉ ተደንግጎ ስለሚገኝ፣ የክልል ወረዳ ፍ/ቤትን ይህን ጉዳይ ማየቱ ስህተት ስላልሆነ እንዲጸናልን በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች በዚህ ጭብጥ ላይ ያቀረበዉ ክርክር ባለመኖሩ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ሰበር ችሎት የግራ ቀኛቸዉን ክርክር እና ለሰበር ቅሬታዉ መነሻ የሆኑትን የሥር ፍ/ቤቶችን ዉሳኔዎች አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥና ተጨማሪ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረበዉ 3ኛ ክስ አመልካች የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 49 (2) በመተላለፍ የስጋ ቤት ንግድ ሥራ ተመዝግቦ የንግድ ሥራ ሲሰራ ቆይቶ የንግድ ፈቃዱን ከሐምሌ 30 ቀን 2010 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 30 ቀን 2011 ዓ.ም ሳያሳድስ የሥጋ ንግድ ሥራ ላይ ተሰማርቶ ሲሰራ የቆየ በመሆኑ ሕገወጥ የንግድ ሥራ በመፈጸሙ ተከሷል የሚል ሲሆን፣ አመልካች ፍ/ቤት ቀርቦ ወንጀል አለመፈጸሙን መብቱን ጠብቆ ክዶ መከራከሩን መዝገቡ ያሳያል፡፡ በዚህ ረገድ ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት ባቀረበዉ የሰዉና የሰነድ ማስረጃ መረዳት እንደሚቻለዉ አመልካች በተሰማረበት የንግድ ሥራ በ2009 ዓ.ም እና በ2010 ዓ.ም ዉስጥ የንግድ ፈቃዱን ሳያሳድስ ሲሰራ የቆየ መሆኑን እንዳስረዳ ያመለክታል፡፡ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠዉ ፍሬ ነገር ይህ ከሆነ ተጠሪ በክሱ ላይ የጠቀሰዉ ፍሬ ነገር አመልካች የንግድ ፈቃዱን ማሳደስ ይገባዉ የነበረዉ ከሐምሌ 30 ቀን 2010 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 30 ቀን 2011 ዓ.ም መሆኑን የሚገልጽ በመሆኑ፣ ዐቃቤ ሕግ በማስረጃ ማስረዳት የሚገባዉ ይኼንኑ ፍሬ ነገር እንጂ ከዚህ ዉጭ የሆነዉን ፍሬ ነገር ማስረዳት አይችልም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች ተጠሪ ባቀረበዉ ክስ መሰረት ያስረዳዉ መሆኑን አለመሆኑን መመርመር ሲገባቸዉ ዐቃቤ ሕግ እንደክሱ አስረድቷል በማለት የደረሱበት ድምዳሜ ከተረጋገጠዉ ፍሬ ነገር ዉጭ መሆኑን ያሳያል፡፡ እንዲሁም የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች በ1ኛ እና 2ኛ ክሶች የተጠቀሱትን የወንጀል ድርጊቶች ለመፈጸም በወ/ሕ/ቁ.23

ሥር በተደነገገዉ አግባብ የሃሳብ ክፍል የሌለዉ ስለሆነ የወንጀል ተጠያቂነት እንደሌለበት አረጋግጠዉ ባለበት፣ 3ኛ ክስም ከእነዚህ ክሶች ጋር ተያያዥነት ያለዉ መሆኑ ተረጋግጦ ባለበት፣ ክሶቹ ተያያዥነት የሌላቸዉና የሚነጣጠሉ መሆናቸዉን በማስረጃ ባልተረጋጠበት ሁኔታ፣ ሶስት ተያያዥነት ባላቸዉ የወንጀል ድርጊቶች መካከል በመከፋፈል አመልካች በሁለቱ ክሶች የወንጀል ተጠያቂነት የለበትም ተብሎ በነጻ እንዲሰናበት መወሰን እና በአንደኛዉ ክስ ደግሞ የወንጀል ኃላፊነት አለበት ተብሎ የጥፋተኛነት እና የቅጣት ዉሳኔ መስጠታቸዉ የሕግ ድጋፍ የለዉም፡፡ በመሆኑም ይህ ሰበር ችሎት በኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80 (3) (ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2 (4) እና 10 (1) (ሐ) ከተሰጠዉ ስልጣን አንጻር አመልካች ያቀረበዉ የሰበር ቅሬታ ሲታይ የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ጉዳይ የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን የሚያመለክት በመሆኑ ቅሬታዉ ተቀባይነት ያለዉ ነዉ ብለናል፡፡

በሌላ በኩል ይህ ሰበር ችሎት የያዘዉ ተጨማሪ ጭብጥ እንደሚከተለዉ የሚታይ ይሆናል፡፡ ችሎቱ በያዘዉ ተጨማሪ ጭብጥ ይህ የወንጀል ድርጊት የፌዴራል ሕግ የሆነዉን አዋጅ ቁጥር 980/2008 በመተላለፍ አመልካች ሕጋዊ ንግድ ፈቃድ ሳይኖረዉ የሥጋ ቤት ንግድ ሥራ ላይ ተሰማርቶ ሲሰራ የነበረና የተከሰሰበት የህግ ድንጋጌ እስከ 15 አመት ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ በመሆኑ፣ ከፌደራል ሕገ መንግስት፣ ከኦሮሚያ ክልል ሕገ መንግስት፣ ከወንጀለኛ መቅጫ ስነስርዓት ሕግ እና ከኦሮሚያ ክልል የፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ አንጻር ሲታይ የክልሉ የወረዳዉ ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ ለማየት የሥረ-ነገር የዳኝነት አለዉ ወይስ የለዉም? የሚለዉን ነጥብ ለመመርመር መሆኑን ያሳያል፡፡ እንደሚታወቀዉ ከደርግ መንግስት ዉድቀ በኋላ የ1987 የኢፌዴሪ ሕገ መንግስት መጽደቅን ተከትሎ ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ የመንግስት ሥርዓትን የዘረጋች መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡ በዚህ መሰረት የሀገሪቱ ሉዓላዊ ስልጣን በፌዴራል እና በክልል መንግስታት መካከል የተከፋፈለ መሆኑን የኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 50 ይደነግጋል፡፡ የፌዴራሉ መንግስት በፌዴራል ጉዳዮች ላይ ስልጣን ያለዉና የፌዴራል ጉዳዮች በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 51 ሥር የተዘረዘረ ሲሆን፣ የክልል መንግስታት ደግሞ ለፌዴራል መንግስቱ በግልጽ ያልተሰጡትን ጉዳዮች ሳይጨምር የክልል ጉዳዮች ላይ ስልጣን ያላቸዉ መሆኑን የሕገ መንግስቱ አንቀጽ 52 ተመልክቶ እናገኛለን፡፡ የፌዴራል እና የክልል መንግስታት የሕግ አዉጭ፣ የአስፈጻሚ እና የዳኝነት ስልጣን የተሰጣቸዉ መሆኑን ማየት ይቻላል (የሕገ መንግስት አንቀጽ 50 (2))፡፡ ከዳኝነት ስልጣን አንጻር ሲታይ በፌዴራልም ሆነ የክልል መንግስታት የዳኝነት ስልጣን ለፍ/ቤቶች ብቻ የተሰጠ መሆኑን በአንቀጽ 79 (1) ሥር ተደንግጓል፡፡ በኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 78 (3) እና 80 (3) (ለ) ደንጋጌዎች ሥር እንደተመለከተዉ የክልል ፍ/ቤቶች በሕገ መንግስቱ የተቋቋሙ ሲሆን፣ እነዚህ ፍ/ቤቶች የክልል የመጀመሪያ ደረጃ (ወረዳ) ፍ/ቤት፣ የዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት፣ የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት እንዲሁም በክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ስር ደግሞ የሰበር ሰሚ ችሎት መኖሩን ይደነግጋል፡፡ በኢፌዴሪ ሕገ መንግስት በተዘረጋዉ የፌዴራል መንግስት አወቃቀር መሰረት ሁለቱም መንግስታት ሆኑ የፌዴራል ፍ/ቤቶች እና የክልል ፍ/ቤቶች በሕገ መንግስቱ ለአንዱ የተሰጠዉን የስልጣን ወሰን በማክበር ሃላፊነታቸዉን መወጣት እንደሚጠበቅባቸዉ ከሕገ መንግስቱ አንቀጽ 50 (8) የሚንገነዘበዉ ጉዳይ ነዉ፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ዉሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በዚህ መሰረት አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ አመልካች የተከሰሰበት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/200 በፌዴራሉ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የወጣ ቢሆንም የኦሮሚያ ክልል ይህን አዋጅ መሰረት በማድረግ በክልሉ ለሚከናወነዉ የንግድ ሥራ የንግድ ፈቃድ የሚሰጥ እና የሚመዘግብ መሆኑን ያላከራከረ ጉዳይ ነዉ፡፡ አሁን ለክርክር መነሻ የሆነዉና አመልካች የተሰማረበት የስጋ ቤት ንግድ ሥራ ሲያከናዉን የነበረዉ በፍቼ ከተማ አስተዳደር ዉስጥ ሲሆን የንግድ ፈቃድም የሰጠዉ እና ከንግድ ፈቃድ ጋር በተያያዘ እርምጃ የሚወስዳዉ የከተማዉ ንግድ ጽ/ቤት መሆኑን እና ከዚህ የንግድ ፈቃድ ጋር በተያያዘ የወንጀል ድርጊት ተፈጽሞ እንደሆነ የወንጀል ኃላፊነት ለማረጋገጥ ስልጣን ያላቸዉ የክልሉ ፖሊስ፣ ዐቃቤ ሕግ እና ፍ/ቤት ባጠቃላይ የክልሉ ፍትህ ተቋማት መሆናቸዉ የሚያከራክር አይደለም፡፡ እነዚህ የፍትሕ ተቋማት ይህን ተግባር የሚያከናዉኑት በፌዴራል ጉዳዮች ላይ በተሰጣቸዉ የዉክልና ስልጣን ሳይሆን በክልል ስልጣናቸዉን መሰረት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑን ይህን የንግድ ፈቃድ የሚሰጠዉ የኦሮሚያ ክልል ውስጥ የሚገኝ ከተማ የሆነዉ የፍቼ ከተማ ንግድ ጽ/ቤት፣ የንግድ ሥራዉንም በሕግ አግባብ የሚቆጣጠረዉ ይኼዉ ጽ/ቤት ሲሆን፣ ከዚህ የንግድ ሥራ ጋር በተያዘዉ በሕግ አግባብ ተገቢዉን ክትትል፣ ቁጥጥርና እርምጃ የሚያደርጉት የክልሉ የመንግስት ተቋማት እንጂ የፌዴራል መንግስት ተቋማት አለመሆኑን በግልጽ ያሳያል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ይህ አዋጅ በፌዴራሉ ሕግ አዉጭ የወጣ ቢሆንም የክልል መንግስታት አዋጁን በራሳቸዉ በዘረጉት የመንግስት መዋቅር ተከትለዉ ተግባራዊ እንደሚያደርጉ የሚያመለክት እንጂ እንደፌዴራል ጉዳይ ተወስዶ የክልል መንግስት በሕገ መንግስቱ በተደነገገዉ የዉክልና ስልጣን መሰረት የሚያከናዉኑ መሆናቸዉን የሚያመለክት ነገር የለም፡፡ ከዚህ አንጻር በፌዴራሉ ሕግ አዉጭ የወጡትን የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ እና የወንጀል ሕግ ማየት ይቻላል፡፡

ይህ ከሆነ ደግሞ በኦሮሚያ ክልል ምክር ቤት የኢፌዴሪ እና የክልሉን ሕገ መንግስታት ባከበረ ሁኔታ የክልሉ ፍ/ቤቶችን የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን ለመወሰን ስልጣን እንዳለዉ ግልጽ ነዉ፡፡ በዚህ መሰረት የኦሮሚ ክልል ምክር ቤት በክልሉ ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 216/2011 አንቀጽ 31 (3) መሰረት የወረዳዉ ፍርድ ቤት ጣራው ከ15 ዓመት በማይበልጥ እሥራት የሚያስቀጣ የወንጀል ጉዳይ ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን እንዳለዉ ደንግጓል፡፡ በመሆኑም የኦሮሚያ ክልል ምክር ቤት (ጨፌ) በዚህ አግባብ ለወረዳዉ ፍ/ቤት የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን በሰጠዉ መሰረት አሁን የተያዘዉ ጉዳይ በወረዳዉ ፍ/ቤት መታየቱ የሚነቀፍበት የህግ አግባብ የለም፡፡ የክልል የወረዳ ፍ/ቤት ይህን የወንጀል ጉዳይ በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣን ተቀብሎ ሰምቶ መወሰኑ እና በየደረጃዉ ያሉት የክልሉ ፍ/ቤቶች የወረዳዉ ፍ/ቤት በዚህ ጉዳይ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣን እንዳለዉ በመቀበል ዋናዉን ጉዳይ አይቶ ተገቢ ነዉ ያሉትን ዉሳኔ መስጠታቸዉ ከፌደራሉ ሕገ መንግስት፣ ከኦሮሚያ ክልል ሕገ መንግስት፣ ከወንጀለኛ መቅጫ ስነስርዓት ሕግ እና ከኦሮሚያ ክልል የፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ አንጻር የሚነቀፍበት አግባብ የለም፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች የተከሰሰበትን የወንጀል ድርጊት መፈጸሙን ተጠሪ በበቂ ሁኔታ በማስረጃ ያስረዳ መሆኑን የዉሳኔዉ ግልባጭ የማያመለክት ሆኖ ባለበት አመልካች ላይ የጥፋተኛነት እና የቅጣት ዉሳኔ መወሰናቸዉ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

**ዉሳኔ**

1. የግራር ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ.40405 በ25/6/2014 ኣ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.64393 በ26/8/2014 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9 (1) መሰረት በአብላጫ ድምጽ ተሽሯል፡፡
2. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.353654 በ07/10/2014 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.404705 የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9 (1) መሰረት በአብላጫ ድምጽ ተሻሽሏል፡፡
3. አመልካች የወንጀል ድርጊት የፈጸመ መሆኑን በበቂ ሁኔታ በማስረጃ ያልተረጋገጠ መሆኑን የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ የሚያመለክት ስለሆነ አመልካች የወንጀል ኃላፊነት ስለሌለበት በነጻ ሊሰናበት ይገባል ብለናል፡፡
4. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
5. አመልካች ከወንጀል ተጠያቂነት ነጻ ስለሆነ ያስያዘዉ የዋስትና ገንዘብ በደረሰኝ እንዲመለስለት ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ/ጋ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

# የልዩነት ሀሳብ

በተራ ቁጥር 4 ላይ የተሰየምኩት ዳኛ በአብላጫ ድምጽ በአመልካች ላይ የቀረበዉን የወንጀል ክስ የመዳኘነት ሥልጣን የኦሮሚያ ክልል ወረዳ ፍርድ ቤት ነዉ ተብሎ በመወሰኑ ስላልተስማማሁ የሚከተሉትን ምክንያቶች መሰረት በማድረግ የልዩነት ሀሳቤን አስፍሬያለሁ፡፡

በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 50 ስር የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ በፌዴራል መንግሥትና በክልሎች የተዋቀረ እንደሆነ፤ የፌዴራልም ሆነ የክልሎች መንግሥታት የሕግ አዉጪነት፣የሕግ አስፈጻሚነትና የዳኝነት ሥልጣን እንዳላቸዉ፤የክልል ምክር ቤት በክልሉ ሥልጣን ስር በሆኑ ጉዳዮች የክልሉ ሕግ አዉጪ አካል እንደሆነና ይህንን ሕገ መንግሥት መሠረት በማድረግ የክልሉን ሕገ መንግሥት የማዘጋጀት፣የማጽደቅ እና የማሻሻል ሥልጣን እንዳለዉ፤በዚህ ሕገ መንግሥት ተወስኖ የተሰጣቸዉን ሥልጣን መሠረት ባደረገ አኳኋን ለፌዴራሉ መንግሥት የተሰጠዉ ሥልጣን በክልሎች መከበር እንዳለበት ለክልሎች የተሰጠዉ ሥልጣን በተመሳሳይ በፌዴራሉ መንግሥት መከበር እንዳለበት ተደንግጓል፡፡በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 55/5 ስር በግልጽ እንደተመለከተዉ የወንጀል ሕግ የማዉጣት ሥልጣን ለፌዴራሉ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተሰጠ ነዉ፡፡ የወንጀል ሕግ ከማዉጣት አንጻር ለክልሎች የተሰጠዉ ሥልጣን በፌዴራሉ መንግሥት የወንጀል ሕግ በግልጽ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ሕግ የማዉጣት ሥልጣን ነዉ፡፡ከዚህ በተጨማሪ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 55/4 ስር እንደተመለከተዉ የንግድ ሕግ የማዉጣት ሥልጣን የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነዉ፡፡

ከላይ በተመለከተዉ መሠረት የወንጀል ሥረ ነገር ሕግ (Substantive Criminal Law) የማዉጣት ሥልጣን በግልጽ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተሰጠ ቢሆንም የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ የማዉጣት ሥልጣን የማን እንደሆነ በሕገ መንግሥቱ አልተገለጸም፡፡የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ የማዉጣት ሥልጣን በአንድ በኩል በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 52/1 መሠረት ለክልል ሕግ አዉጪ የተተወ ሥልጣን ነዉ የሚል ክርክር ሲነሳ ይሰማል፡፡በሌላ በኩል ደግሞ የሥነ ሥርዓት ሕግ ዋናዉን የወንጀል ሥረ ነገር ሕግ ለማስፈጸም የሚወጣ ሕግ እንደመሆኑ እንደተቀጽላ ሕግ(የዋናዉ የወንጀል ሕግ አካል) ተደርጎ ስለሚቆጠር የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ የማዉጣት ሥልጣን በተለይ ለፌዴራል ወይም ለክልል ሕግ አዉጪ የተሰጠ ሥልጣን ነዉ ብሎ መደንገግ ሳያስፈልግ የወንጀል ሕግ የማዉጣት ሥልጣን ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በመሰጠቱ ይህንን ሕግ የሚያስፈጽም ሥነ ሥርዓት ሕግ የማዉጣት ሥልጣንም የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተፈጥሯዊ ሥልጣን ነዉ የሚል ክርክር ይነሳል፡፡እኔም የወንጀል ሕግ የማዉጣት ሥልጣን ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተሰጠበት ምክንያት በሚገባ ይሳካ ዘንድ እና የወንጀል ሕግ የሰዉን፣የማኅበራዊ ኑሮ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ደረጃን፣የዘርን፣የብሔርን፣የብሔረሰብን፣የቀለምን፣የጾታን የቋንቋን፣ የሃይማኖትን፣ የፖለቲካ ወይም ሌላ አስተሳሰብን መሰረት በማድረግ ወይም በሌላ በማንኛዉንም አቋም ልዩነት ሳያደርግ በአገሪቱ በሁሉም ሥፍራ በእኩልነት፣ተገማች እና ወጥ በሆነ አግባብ ተፈጻሚ እንዲሆን ለማድረግ፤እንዲሁም በወንጀል ሕግ አንቀጽ 4 ስር ከተደነገገዉ ልዩ ሁኔታ ዉጭ በወንጀል አድራጊዎች መሀከል ልዩነት ሳይደረግ ሕጉን ተግባራዊ ማድረግ ይቻል ዘንድ የወንጀል ሕግ ማስፈጸሚያ ሥነ ሥርዓት ሕጉን የማዉጣት ሥልጣን የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነዉ ብዬ አምናለሁ፡፡ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሎች ምክር ቤቶች በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 55/5 ስር በተሰጣቸዉ ሥልጣን መሠረት በፌዴራሉ የወንጀል ሕግ በግልጽ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ የወንጀል ሕግ ሲያወጡ በዚህ ሥልጣናቸዉ የሚያወጡትን የወንጀል ሕግ ለማስፈጸም የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ የማዉጣት ሥልጣን አላቸዉ የሚል እምነት አለኝ፡፡

የፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን በጠቅላላዉ በተለይ ደግሞ የፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ዳኝነት ሥልጣን የሚወሰነዉ በሥነ ሥርዓት ሕግ(ኮድ)፣ በፍርድ ቤቶች አዋጆች እና አንድን ድርጊት ወንጀል አድርገዉ በሚደነግጉና ሥነ ሥርዓታዊ ባህሪይ ባላቸዉ ልዩ ልዩ ሕግጋት ነዉ፡፡በዚህ መሠረት በነባሩና በ1954 በወጣዉ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1/1954 (ከዚህ በኂላ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ተብሎ የሚጠቀስ) አባሪ በሆነዉ አንደኛ ሠንጠረዥ ላይ አገራችን አህዳዊ ሥርዓት በምትከተልበት ጊዜ የነበረዉን የፍርድ ቤቶች አደረጃጀት በመከተል ለተደራጁ ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ዳኝነት ሥልጣን ክፍፍል ተደርጓል፡፡ በዚህ ሕግ በአባሪ ሠንጠረዥ አንድ የተመለከተዉን የዳኝነት ሥልጣን ክፍፍል ለማሻሻል በወጣዉ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ማሻሻያ ደንብ ቁጥር 17/1967 ላይ በሌሎች ሕጎች የተወሰነዉ የወንጀል ቅጣት ከአስር ዓመት ጽኑ እስራት በላይ የሚያስቀጣ ሲሆን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስረ ነገር ዳኝነት ሥልጣን እንደሚኖረዉና ከአስር ዓመት በታች በሆነ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ወንጀል የመዳኘት ሥልጣን ደግሞ የወረዳ እና የአዉራጃ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን እንደሆነ ተመልክቷል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ከላይ በተገለጸዉ መሠረት የስረ ነገር ዳኝነት ሥልጣን ክፍፍል የሚያደርገዉን ነባሩን የሥነ ሥርዓት ሕግ የሚያሻሽል ሕግ ማዉጣት ያለበት የፌዴራል ሕግ አዉጪ አካል ነዉ ወይስ የክልል ሕግ አዉጪ አካል የሚለዉ ጥያቄ መነሳትና ምላሽ ማግኘት አለበት፡፡ ይህንን ጥያቄ በአግባቡ ለመመለስ ይህ ነባር የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ የእንደፌዴራል ሕግ የሚቆጠር ነዉ ወይስ እንደክልል ሕግ የሚቆጠር ነዉ የሚለዉን በቅድሚያ መመርመር ያስፈልጋል፡፡በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 2/3 ስር የፌዴራሉ መንግሥት ሕጎች ማለት ሕገ መንግሥቱን የማይቃረኑና በሕገ መንግሥቱ ላይ የተጠቀሱትን በፌዴራል መንግሥቱ ሥልጣን ክልል ስር ያሉ ጉዳዮችን የሚመለከቱ በሥራ ላይ ያሉ ነባር ሕጎችን እንደሚጨምር ተመልክቷል፡፡በተመሳሳይ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2/2 ስር የፌዴራል መንግሥት ሕጎች ማለት በፌዴራል መንግሥቱ ሥልጣን ክልል ስር የሚወድቁ ጉዳዮችን የሚመለከቱ በሥራ ላይ ያሉ ሕጎችን እንደሚጨምር ተመልክቷል፡፡ከዚህ ትርጓሜ በመነሳትና

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ያወጡት የማዕከላዊ መንግሥት የሕግ መወሰኛና የሕግ መምሪያ ምክር ቤቶች በመሆናቸዉ፣ እነዚህን ምክር ቤቶች በዋናነት የተካዉ ምክር ቤት በሕገ መንግሥቱ የተመለከተዉን የፌዴራልና የክልል መንግሥታት ሥልጣን ክፍፍል ከግምት ማስገባት ሳይረሳ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በመሆኑ ከላይ በተገለጸዉ መሠረት የወንጀል ሕጉን የሚያስፈጽም ሥነ ሥርዓት ሕግ የማዉጣት ሥልጣን የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በመሆኑ ነባሩ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ የፌዴራሉ መንግሥት ሕግ ነዉ፡፡

በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 50/5 መሠረት የክልል ምክር ቤት ሕግ የማዘጋጀት፣የማጽደቅና የማሻሻል ሥልጣን የሚኖረዉ በክልሉ ሥልጣን ስር የሆኑ ጉዳዮችን በሚመለከት ብቻ ነዉ፡፡ከዚህ ዉጭ የክልል ምክር ቤት በሕገ መንግሥቱ ለፌዴራል መንግሥት የተሰጠ ጉዳይ በተመለከተ በነባር ሕጎች የተደነገገዉን የሚያሻሽል፣ የሚለዉጥ ወይም የሚሽር ሕግ ማዉጣት አይችልም፡፡ በመሆኑም የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት ሕግ የማዉጣት ሥልጣን በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55/5 መንፈስና ዓላማ መሠረት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተሰጠ ሥልጣን በመሆኑ ነባሩና አሁን በሥራ ላይ ያለዉ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ እንደ ፌዴራል ሕግ የሚቆጠር ስለሆነ የክልል ምክር ቤት ከክልል የወንጀል ጉዳይ ጋር በተያያዘ ካልሆነ በስተቀር ይህንን ሕግ የሚያሻሽል፣የሚለዉጥ ወይም የሚሽር ሕግ ማዉጣት አይችልም፡፡

ወደተያዘዉ ጉዳይ ስመለስ በአመልካች ላይ የቀረበዉ ሦስተኛ ክስ አመልካች የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 49 (2) በመተላለፍ የተሰጠዉን ፈቃድ የስኳር ንግድ ለመነገድ የማይፈቅድ ሆኖ እያለ ለስኳር ንግድ የተሰጠዉ ፈቃድ ያለዉ በማስመሰል እየተንቀሳቀስ እያለ ስለተያዘ በፈጸመዉ የሕገወጥ ንግድ መስራት ወንጀል ተከሷል የሚል ነዉ፡፡ የንግድ ሥራ የሚመለከት ሕግ ማዉጣት የፌዴራል መንግሥት ሥልጣን ነዉ፡፡ይህ አመልካች የተከሰሰበት ሕግ የወጣዉም በፌዴራሉ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነዉ፡፡ነገር ግን የክልል መንግሥት ንግድ ቢሮ የኢትዮጵያ የንግድ ሥራ ፈቃድ መስጫ መደብ መመሪያ ላይ የተደነገገዉን በመከተል የንግድ ሥራ ፈቃድ መስጠትና በሰጠዉ የንግድ ፈቃድ መሠረት የንግድ ሥራ እየተሰራ መሆን አለመሆኑን የመቆጣጠር አስተዳደራዊ ሥራ የመሥራት ሥልጣን በሕጉ ተሰጥቶታል፡፡

በሌላ በኩል በዚህ አዋጅ ላይ ሕግ አዉጪዉ በወንጀል የሚያስቀጡ ድርጊቶችን ደንግጓል፡፡የጸና የንግድ ሥራ ፈቃድ ሳይኖር በንግድ ሥራ መሠማራት ወይም በንግድ ሥራ ፍቃዱ እንዲሰራ ከተፈቀደዉ የንግድ ሥራ ዉጭ መሥራት ወንጀል እንደሆነና የሚያስቀጣዉም ቅጣት በዚሁ አዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 49/2 ስር ተደንግጓል፡፡ በዚህ መልኩ የተደነገገዉ በፌዴራል ሕግ ላይ መሆኑ ግልጽ ነዉ፡፡ነገር ግን በአንዳንድ በፌዴራል መንግሥት በወጡ ሕግጋት ላይ ለአብነት በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 139/1 ስር የግል ሥራ ክርክር የመዳኘት ሥልጣን ለክልል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንደተሰጠ በአዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 49 ስር የተደነገገዉን ወንጀል የመዳኘት ሥልጣን

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የየትኛዉ ፍርድ ቤት እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 980/2008 ላይ አልተደነገገም። ሆኖም በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 4 ስር ከተደነገጉት የወንጀል ጉዳዮች ዉስጥ ይህ ወንጀል በግልጽ ስላልተጠቀሰ በመርህ ደረጃ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ከሚዳኙ የወንጀል ጉዳዮች ዉስጥ የሚካተት አይደለም። በልዩ ሁኔታ ግን ወንጀሉ የተፈጸመዉ በአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደር ከተሰጠ የንግድ ፈቃድ ጋር በተያያዘ ወይም ፈቃድ ሳይኖር የንግድ ሥራ የተሠራዉ በእነዚህ የከተማ አስተዳደሮች ዉስጥ የሆነ እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 3(1/ሀ እና ሐ) እና 12/2 እንዲሁም አንቀጽ 15/2 ስር በተደነገገዉ መሠረት ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ይሆናል።

በዚህ ጉዳይ አመልካች ወንጀል ፈጸመ የተባለዉ የኦሮሚያ ክልል መንግሥት የሰጠዉ የንግድ ፈቃድ ከሚፈቅድለት ማዕቀፍ ዉጭ የንግድ ሥራ ሠርቷል በሚል በመሆኑ በክልሉ ፍርድ ቤቶች ሊታይ የሚችል የወንጀል ጉዳይ ነዉ።ነገር ግን የክልሉ ፍርድ ቤቶች በፌዴራል መንግሥት በወጣ ሕግ ላይ የተደነገገዉን የወንጀል ክስ ክርክር ተቀብለዉ ሲዳኙ ድርጊቱን ወንጀል አድርጎ በደነገገዉ ልዩ ሕግ ላይ ስለዳኝነት ሥልጣንና ስለሚመሩበት ሥነ ሥርዓት በግልጽ ያልተደነገገ እንደሆነ በነባሩ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ (ማሻሻዉን ጨምሮ) ላይ የተደነገገዉን የፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ዳኝነት ሥልጣን ክፍፍል እና ስለክርክር አመራር የተዘረጋዉን ሥነ ሥርዓት መከተል ይጠበቅባቸዋል።ምክንያቱም ክልሎች በፌዴራሉ የወንጀል ሕግ የተደነገገዉን ወይም በልዩ ሕግ የተደነገገዉን የወንጀል ጉዳይ ለመዳኘት የየራሳቸዉን አዲስ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ለማዉጣትም ሆነ ነባሩን የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ለማሻሻል የሚያስችል ሥልጣን ስለሌላቸዉ እና ይህንን እንዲያደርጉ መፍቀድ የፌዴራል ሕግ በአገሪቱ ግዛት በሙሉ ተገማችና ወጥ በሆነ አግባብ እንዳይተገበር ስለሚያደርግ እና በሁሉም ዜጎች ላይ በእኩልነት ተፈጻሚ እንዳይሆን ስለሚያደርግ ነዉ።

እንዲሁም በአመልካች ላይ በቀረበዉ ሦስተኛ ክስ የተጠቀሰዉ የአዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 49/2 ከሰባት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ነዉ። የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት አንደኛ ሠንጠረዥ ለማሻሻል በወጣዉ ደንብ ቁጥር 17/1997 ላይ እንደተደነገገዉ በልዩ ሕጎች የተወሰነዉ ቅጣት ከአስር ዓመት ጽኑ እስራት በላይ የሚያስቀጣ ሲሆን ክሱን ተቀብሎ ለመዳኘት የስረ ነገር ዳኝነት ሥልጣን ያለዉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነዉ። ከዚህ ጋር በተያያዘ በኦሮሚያ ክልል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 216/2011 አንቀጽ 31/3 ስር እስከ አስራ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት የሚያስቀጡ ወንጀሎችን የመዳኘት ስረ ነገር ሥልጣን ለወረዳ ፍርድ ቤት የተሰጠዉን በደንብ ቁጥር 17/1997 ከተደነገገዉ፣በሕገ መንግሥቱ ከተዋቀረዉ ዳኝነታዊ ፌዴራሊዝም እና ሕግ ከማዉጣት ጋር በተያያዘ የተደረገዉን የሥልጣን ክፍፍል እንዲሁም በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 3፣4፣12 እና 15 ላይ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሚዳኝ የወንጀል ጉዳዮች እንደሆነ ከተደነገገዉ ጋር በማገናዘብ መመርመር ያስፈልጋል።

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የኦሮሚያ ክልል ሕግ አዉጪ አካል(ጨፌ) በዋናነት የኦሮሚያ ክልል ፍርድ ቤቶችን አዋጅ ቁጥር 216/2011ን ያወጣዉ በክልል ጉዳዮች ላይ የክልሉ ፍርድ ቤቶች የሚኖራቸዉን የዳኝነት ሥልጣን ለመወሰን መሆኑ ግልጽ ነዉ፡፡በመሆኑም በአዋጁ አንቀጽ 31/3 ስር እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደረስ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ወንጀል የሚመለከት የሚቀርብ ክስ የመዳኘት ሥልጣን የወረዳ ፍርድ ቤት ነዉ ተብሎ የተደነገገዉ በክልል የወንጀል ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆን እንደሆነ ተቆጥሮ ተግባራዊ ማድረግ ይገባል፡፡ እንዲሁም በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ አንቀጽ 3፣4፣12 እና 15 ላይ በተደነገገዉ መሰረት በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሚዳኙ ወንጀሎች ናቸዉ ተብሎ በግልጽ ባልተመለከተ እና ለክልል ፍርድ ቤቶች የተተተወ የወንጀል ጉዳይ በሚመለከት፤ በፌዴራል ልዩ ልዩ ሕግጋት ላይ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሚዳኙ ወንጀሎች ናቸዉ ተብሎ በግልጽ ባልተመለከተ የወንጀል ጉዳይ እና በነባር የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ (ማሻሻዉን ጨምሮ) የተደነገገዉን የፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ዳኝነት ሥልጣን ክፍፍል በማይቃረን አግባብ ድንጋጌዉ ተግባራዊ መሆን ይኖርበታል፡፡

ሲጠቃለል በአመልካች ላይ ከተመሠረቱት ሦስት ክሶች መካከል አንደኛ እና ሁለተኛ የወንጀል ክሶች እንደቅደም ተከተላቸዉ በክልሉ ምክር ቤት የታክስ አስተዳደርን ለመወሰን የወጣዉን አዋጅ ቁጥር 203/2009 አንቀጽ 125/1 እና በተመሳሳይ በክልሉ ምክር ቤት የተርን ኦቨር ታክስ ለማስከፈል የወጣዉን አዋጅ ቁጥር 75/1995 አንቀጽ 26 በመተላለፍ የተከሰሰበት ወንጀል በመሆኑ የክልል ወንጀል ጉዳዮችን የሚመለከቱ ስለሆኑ በኦሮሚያ ክልል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 216/2011 አንቀጽ 31/3 መሠረት የግራር ጃርሶ ወረዳ ፍርድ ቤት እነዚህን ሁለቱን ክሶች የመዳኘት ሥልጣን ሥላለዉ እነዚህን ክሶች ከመዳኘት አንጻር የተፈጸመ ስህተት ስለሌለ በአብላጫ ድምጽ በተደረሰበት ድምዳሜ ከዉጤት አንጻር እስማማለሁ፡፡ነገር ግን ሦስተኛዉን የወንጀል ክስ በተመለከተ አመልካች ተላልፏል የተባለዉ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 በፌዴራል መንግሥቱ የወጣ ሕግ በመሆኑ፣በዚህ ሕግ ወንጀል ነዉ ተብሎ የተደነገገዉ ተፈጽሞ ሲገኝ የሚዳኝበት አግባብ በመላዉ አገሪቱ ግዛት እና በሁሉም ዜጎች ላይ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 3 እና 4 ስር በተደነገገዉ መሠረት የእኩልነትና የተገማችነት መርህን ባከበረ መልኩ በወጥነት ተፈጻሚ መሆን ስለሚገባዉ የፌዴራሉ የሕግ አካል በሆነዉ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ሕግ (ማሻሻዉን ጨምሮ) የተደነገገዉን በተከተለ አኳኋን ሥልጣን ባለዉ ፍርድ ቤት ቀርቦ መታየት ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም አመልካች ፈጽሟል ተብሎ የተከሰሰበት ወንጀል በአዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 49/2 ላይ እንደተመለከተዉ ከአስር ዓመት በላይ በሆነ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ በመሆኑ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት አንደኛ ሠንጠረዥ ለማሻሻል በወጣዉ ደንብ ቁጥር 17/1997 ላይ በተደነገገዉ መሠረት ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን የክልል ወረዳ ፍርድ ቤት ሳይሆን የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስረ ነገር ዳኝነት ሥልጣን ነዉ፡፡ስለሆነም በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሀ) እና 10(1/ሐ) መሰረት የግራር ጃርሶ ወረዳ ፍርድ ቤት ክሱን ተቀብሎ የዳኘዉ የሥረ ነገር ዳኝነት ሥልጣን ሳይኖረዉ ነዉ ተብሎ ሊሻር ይገባል ብዬ ስለማምን በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

እ/ጋ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 237478

ጥቅምት 25 ቀን 2016 ዓ.ም

**ዳኞች** ፡-ሽመክት አሰፋ

ገበየሁ ፈለቀ

አለማየሁ ሹናራ

ተናኘ ጥላሁን

ዘውዲቱ ታደሰ

አመልካች፡- ሶስና ሀይሉ ብርሀኔ -አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ጆን ፒጂፐርስ -ጠበቃ አቶ ኤፍሬም ዘውዴ -ቀረቡ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ሲሆን ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሕዳር 19 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 133829 ታህሳስ 28 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ብይን እና በየካቲት 17 ቀን 2014 ዓ.ም በተሰጠው ውሳኔ እንዲሁም በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በ/ቁ 287342 ህዳር 15 ቀን 2015 ዓ.ም የጸናው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸው በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው መነሻነት ነው፡፡ ጉዳዩ የንብረት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር ተጠሪ ከሳሽ እንዲሁም አመልካች ተከሳሽ ነበሩ፡፡

ተጠሪ ጥቅምት 13 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት ክስ ይዘት ባጭሩ ተጠሪ ወላጅ አልባ የሆኑ ህጻናትን በጉዲፈቻ በመውሰድ የማሳድግ እና የማስተምር ስሆን በመሀል ህጻናትን በጉዲፈቻ ከኢትዮጵያ ወደ ሌላ

**ማስታወሻ**፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓለማአየገለግልም!

ሀገር መውሰድ የሚከለክል ህግ በመውጣቱ በዚሁ ሀገር ውስጥ ህጻናቱን እንድትንከባከብ ፣ ምግብ የሚያዘጋጅላቸው ሰው በማስፈለጉ ተከሳሽ ይህንን ስራ እንድታከናውን ከቀን 23/04/2005 ዓ.ም ጀምሮ በወር 60(ስልሳ) ዩሮ ለመክፈል ተስማምቼ የቅጥር ውል ፈጽሜያለሁ፡፡ ለህጻናቱ መኖሪያ ቤት ለመግዛት አስቤ ነገር ግን የማይንቀሳቀስ ንብረት በስሜ መግዛት ስለማይፈቀድልኝ አመልካችን እንድትፈልግ ተነጋግረን 3,500,000 (ሶስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ብር) የሚሸጥ ቤት አጊንቻለሁ ይዘህ ና ብላኝ ከኔዘርላንድ ወደ ኢትዮጵያ በቀን 14/05/2010 ዓ.ም ስገባ 110,000 (አንድ መቶ አስር ሺህ ) ዩሮ በኔዘርላንድ ኤርፖርት ዲክሌር አድርጌ ይዤ መጥቼ አመልካች በቀን 18/05/2010 ዓ.ም በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 10 የቤት ቁጥር አዲስ ባለ ሶስት ፎቅ መኖሪያ ቤት በ2,000,000 (ሁለት ሚሊዮን) በስሟ ገዝታ ቀሪውን 1,5200,000 አልመለሰችልኝም፡፡

ተጠሪ ከኔዘርላንድ ሀገር በየወሩ ለልጆቹ አስቤዛ፣ ት/ቤት ክፍያ፣ የቀለብ ወጪ የልብስ መግዣ በአጠቃላይ 81,044 (ሰማንያ አንድ ሺህ አርባ አራት) ብር የምልከውን ገንዘብ ለግል ጥቅሟ በማዋል ልጆቹን እየደበደበች ሁለት ህጻናቶች ከቤት እንደወጡ አድርጋለች፤ ልጆቹ ወደ ት/ቤት ማመላለሻ መኪና በማስፈለጉ በቀን 22/05/2007 ዓ.ም 15,000 ዩሮ በአቢሲኒያ ባንክ ለአመልካች ልኬላት በስሟ የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 2-አ/አ 88399 የሆነ ኮሮላ መኪና በብር 400,000 (አራት መቶ ሺህ) ብር ገዝታ መኪናውን ወደ ኮድ 3 ቀይራ ከተገዛበት አላማ ውጪ ራይድ እሰራችበት ትገኛለች፡፡ እንዲሁም ለቤት ቁሳቁሶች የሚሆን ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ በአጠቃላይ 76,848 (ሰባ ስድስት ሺህ ስምንት መቶ አርባ ስምንት ብር) በአመልካች ገንዘብ የተገዙ ናቸው፡፡ ስለሆነም 1/በተከሳሽ ስም በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 10 የቤት ቁጥር አዲስ የሆነ ባለሶስት ፎቅ ይዞታ የተጠሪ ነው ተብሎ አመልካች እንድታስረክበኝ፣ 2/የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ -3 B 39086 አ/አ መኪና እንድታስረክበኝ፣ 3/ከቤቱ መግዣ ከሰጠኋት ገንዘብ ላይ ቀሪውን ገንዘብ 1,520,000 (አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሀያ ሺህ) ብር እንድትመልስኝ ፣ 4/የቤት ቁሳቁሶችን እንድትመልስልኝ በዚህ ክስ ምክንያት ያወጣሁትን ወጪ እንድትከፍለን ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

አመልካች ታህሳስ 4 ቀን 2014 ዓ.ም ካቀረቡት መልስ ጋር የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የፍሬ ነገር ክርክር ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም ህጻናቱ ከአመልካች ጋር ህጋዊ የሆነ ግንኙነት የላቸውም ፣ ከህጻናቱ ወላጆች ጋር ያደረጉት የጉዲፈቻ ስምምነት የለም፤ የውጭ ድርጅት እንደመሆኑ ይህንን ስራ ለመስራት በኢትዮጵያ ውስጥ ለመስራት የሚያስችል የምዝገባ የምስክር ወረቀትና የስራ ፍቃድ የላቸውም፤ በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 10 የቤት ቁጥር አዲስ የሆነ ቤት የአመልካች የግል ሀብት የምስክር ወረቀቱም በስመ የተመዘገበ በመሆኑ በፍ/ሕ/ቁ 1195/1/ መሰረት የተሸለ መብት ያለን አመልካች ነኝ፤ ተጠሪ በፍ/ህቁ 1196

መሰረት ተቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ የቤቱ ባለሀብት እንዳልሆንኩ አላስተባበሉም፤ ገንዘብ ሰጥቻለሁ ይመለስልኝ ብሎ ዳኝነት ከመጠየቅ በቀር አኔ በሰጠኋት ገንዘብ ቤት ገዝታለች ትመልስልን በማት ያቀረቡት ክርክር የክስ ምክንያት የለውም፡፡

በፍ/ህ ቁ 2723 እና 1723 መሰረት በቤቱ ላይ ያቋቋሙት ውል የሌለ በመሆኑ ያቀረቧቸው ምክንያቶች ተቀባይነት የላቸውም፤ የሰሌዳ ቁትሩ 3-B2906 አ/አ የሆነው ተሽከርካሪ በአመልካች ስም ተመዝግቦ የሚገኝ የግል ሀብቴ ነው፤ የተገዛው በተጠሪ ገንዘብ የተገዛ አይደለም እንጂ ተገዝቶ ቢሆን እንኳን በፈቃዳቸው በስሜ ገዝተው የሰጡትን መኪና መልሽ ለማለት የሚችሉበት የህግ አግባብ የለም፤ ተጠሪ አመልካች 3,500,000 (ሶስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ) ብር የሰጡ ስለመሆኑ ያቀረቡት የብድር ውል ወይም የገንዘብ ዕዳ ያለብን መሆኑን የሚያረጋግጥ በጽሁፍ የተፈራረምኩት የሰነድ ማስረጃ ሳያቀርቡ ገንዘብ ይመለስልኝ በማለት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፤ የቤት ቁሳቁሶቹ

በአመልካች ተገዛ የተከሳሽ የግል ሀብት ነው፤ ስለሆነም ተጠሪ ያቀረቡት ክስ የህግና የማስረጃ ድጋፍ የሌለው ክስ በመሆኑ ክሱ ውድቅ ተደርጎ ወጪና ኪሳራ ጋር ይወሰንልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍሬ ጉዳዩን በማስረጃ የማጣራትና የመመዘን ስልጣን ያለው የስር ፍ/ቤት የቀረበለትን የሰነድ እና የሰው ማስረጃዎች የግራቀኙን የጽሁፍና የቃል ክርክር ሰምቶ የተከሳሽን የመጀመሪያ ደረጃ በብይን ውድቅ ካደረገ በኋላ ፣ በፍሬ ጉዳይ ላይ 1. በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 10 የቤት ቁጥር አዲስ የካርታ ቁጥሩ ቦሌ 10/43/9/11/49694/18781 የሆነው መኖሪያ ቤት ፣ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 2-88399 ወይም ኮድ -3-B 29086 አ.አ የሆነው ተሽከርካሪ የተገዛው በአመልካች ገንዘብ ነው? ወይስ አይደለም? አመልካች ቤቱ ከተገዛበት ገንዘብ ውጪ ብር 1,520,000 (አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሀያ ሺ.ህ) ከተ ሪ ወስዳለች? ወይስ አልወሰደችም? እንዲሁም በክሱ ላይ የተዘረዘሩት የቤት ቁሳቁሶች በከሳሽ የተገዙ ናቸው? አይደሉም?የሚለውን ጭብጥ ለይቶ በመያዝ የግራቀኙን ምስክሮች ከሰማና በግራቀኙን የቀረቡትን ማስረጃዎች ከመረመረ በኋላ ከተቋማቱ በመጡት ምላሾች እና በቀረቡት ምስክሮች ንብረቶቹ በተጠሪ ከውጪ በገቡ እንዲሁም በባንክ በተላኩ እና ከተጠሪ ለአመልካች በተሰጠ ገንዘብ የተገዙ ስለመሆኑ በተሻለ ሁኔታ አስረድተዋል በማለት በአ/አ ከተማ ወረዳ 10 የቤ.ቁ አዲስ በካርታ ቁጥሩ ቦሌ 10/43/9/11/49694/18781 የሆነው መኖሪያ ቤት ፣ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 2-አ.አ 88399 ወይም ኮድ -3-B 29086 አ.አ በአመልካች ስም ተመዝግቦ የሚገኘው ተሽከርካሪ አመለልካች ለተጠሪ ያስረክቡ፣ ከቤቱ ሽያጭ የተረፈውን ገንዘብ ብር 1520000 (አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሀያ ሺ.ህ ብር) ክሱ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍሉ፣ ግምታቸው 76,848 የሆነ የቤት ዕቃ ንብረቶች ተከሳሽ ለከሳሽ እንዲያስረክቡ ወጪና ኪሳራ እንዲከፍሉ በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች የህንን ውሳኔ በመቃወም ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ አቤቱታውን አቅርው ውሳኔው ሳይለወጥ ቀርቷል፡፡

አመልካች ሕዳር ከ ቀን 2014 ዓ.ም ጽፎ ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ይህን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ሲሆን አመልካች በስር ፍ/ቤት በፍ/ብ/ህ/ቁ 1206 መሰረት የመፋለም ክስ አቅርቤ ፍ/ቤቱ የመፋለም ክሱን ወደ አላግባብ መበልጸግ ክርክር በመለወጥ አመልካች በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2162 መሰረት አለላግባብ በልጽጋለች በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመ ነው፡፡ አመልካች አለአግባብ አልበለለጸኩም እንጂ በልጽጋለች በማለት አስረድተዋል ቢባል እንኳን ተጠሪ ሊጠይቁ የሚገባቸው ኪሳራ ሆኖ እያለ ባልተከሰስኩበት የህግ ማዕቀፍና ባልተከራከርኩበት ነገር ላይ የጭብጥ አመሰራረት ስርዓትን በመጣስ አመልካች በስሜ ተመዝግቦ የሚገኝ ቤት ባለሀብት እንደሆንኩ ግምት እንደሚያስወስድ መሆኑ ግልጽ ሆኖ ሳለ በሌላ ሰው ሀብት በሆነ ነገር በመገልገል ጥቅም አግኝታበታለች ባገኘችበት ጥቅም እና ተጠሪ ላይ በደረሰው ጉዳት ኪሳራ መክፈል አለባት በማለት የሰጠው ውሳኔ የማስረጃ መሰረት የሌለውና መሰረታዊ የህግ ስህትት ያለበት ነው፡፡የቤቱ ይዞታ በአመልካች ስም ተመዝግቦ እያለ የስር ፍ/ቤቱ ቤቱ የተገዛው በተጠሪ ገንዘብ ለ3ኛ ወገን ጥቅም ነው ካርታው የተሰጠውም ከደንብ ውጪ በሆነ አሰራር ነው በማለት የደረሰበት መደምደሚያ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡ ተጠሪ ከውጪ አገር ዩሮ ይገኘ ገብቻለሁ ያሉበት አግባብ በብሔራዊ ባንክ መመሪያ አግባብ የገባ ስለመሆነ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ በህግ ፊት የሚጸና አይደልም፤ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት

ሰ/ሰ/ችሎት በሰ/መ/ቁ 33831 ፣ 67011 እና 75414 በሰጣቸው አስገዳጅ የህግ ትርጉሞች የማንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነት የሚረጋገጠው በሚመለከተው የመንግስት አካል በሚሰጠው የምስክር ወረቀት መሆኑ ተረጋግጦ እያለ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1196 መሰረት የምስክር ወረቀቱ ውጤት የሌለው ስለመሆኑ በተጠሪ በኩል የቀረበ ተቃራኒ ክርክርና ማስረጃ በሌለበት የስር ፍ/ቤቱ ይህንን ድንጋጌ በመጥቀስ የሰጠው ዳኝነት በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4)(ለ) ድንጋጌ መሰረት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ነው፡፡

ተጠሪ ዩሮውን ከውጭ ሀገር ሲያስገቡ ጉምሩክ ሰነዱም በአዋጅ ቁጥር 922/2008 አንቀጽ 7 አግባብ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ወይም በሌላ በሚመለከተው መንግስታዊ አካል በኩል ያልተረጋገጠ በመሆኑ በማስረጃ ሊያዝ አይገባም፤ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመግዛት ተብሎ ዲክሌር የተደረገ አይደለም፤ ተጠሪ ሰነዱን በአዋጅ ቁጥር 922/2008 አንቀጽ 7 አለማረጋገጡን አምኖ በከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 345 ለማቅረብ ጠይቆ ተጨማሪ ማስረጃ ጥያቄ ላይ ካከራከረን በኋላ ሥነስርዐቱን ተከትሎ የቀረበ አይደለም በሚል በብይን ውድቅ አድርጎት የነበረ ቢሆንም በውሳኔው ላይ ይህንን ብይን ውጤት አልባ በማድረግ በህጉ መሰረት ያልተረጋገጠ የውጭ አገር ሰነድ ህጋዊ ተቀባይነትና ክብደት አግኝቶ

የአመልካችን የንብረት መብት በመጣስ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል፡፡

ተጠሪ ከባንክ ተበደርኩ የሚሉት 110,000.0 ዩሮ ወይም በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የጠቀሱት 105,000 ዩሮ ወደ ኢትዮጵያ ያስገቡት ለሚመለከተው አካል በህጉና በታወቀው አሰራር አሳውቀው (ዲክሌር) አድርገው ስለመሆኑ ማስረጃ ሳያቀርቡ የተሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡ የስር ፍ/ቤት የማይንቀስ ንብረቱ በተጠሪ ገንዘብ የተገዛ ስለመሆኑ በምስክሮች ተረጋግጧል በማለት የደረሰበት ድምዳሜ የማይንቀሳቀስ ንብረትን በጥሬ ገንዘብ ፣ በጉልበትና በእውቀት አፍርቻለሁ በማለት ይህንኑ በሰው ማስረጃ የማስረዳትና ንብረቱ የሚታወቅበትን የሰነድ ማስረጃ፣ በሰው ምስክርነት ዋጋ ማሳጣት ከንብረት ሕገመንግስታዊ መብት ጋር የማይሄድና ህገመንግስቱን የሚጥስ የማስረጃ ህግን መርህ ውስጥ የማያስገባ መሆኑን የኢ.ፌ.ድ.ሪ ፌደሬሽን ምክር ቤት ጥቅምት 2 ቀን 2009 ዓ.ም በተካሄደው 5ኛ የስራ ዘመን 2ኛ አመት 1ኛ መደበኛ ስብሰባ በአመልካች ቄስ ወርቁ ዳዲሞስና በተጠሪዎች ወ/ሮ ሰብለወንጌል ወርቁና በወ/ሮ ማሚቴ ወሬራ መካከል በነበረው የማይንቀሳቀስ ንብረት ሕገመንግስታዊ ክርክር ውሳኔን የሚጥስ በመሆኑ ሊታረም ይገባል፡፡ ተጠሪ ገንዘብ ስለሰጠሁ ቤት ይመለስልኝ በማለት ያቀረቡት ክርክር የክስ መክንያት የሌለውና አመልካች ቤቱን የገዛሁበት የሽያጭ ውል ጸንቶ ባለበት ተጠሪ ውል ይፍረስልኝ በማለት ያቀረቡት ክስ እና የጠየቁት ዳኝነት የሌለ በመሆኑ በህግ ጸንቶ ያለ የቤት ሽያጭ ውል መሰረት በማድረግ አመልካች በቤቱ ላይ ያገኘሁት የባለሀብትነት መብት የሽያጭ ውሉ ፈራሽ እስካልተደረገ ድረስ የቤቱን ባለሀብትነት የሚቀጥል በመሆኑና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 23331 ላይ በህግ ጸንቶ ያለ የሽያጭ ውልን መሠረት በማድረግ የተገኘ መብት ውሉ ፈራሽ እስካልተደረገ ድረስ የሚቀጥል ስለመሆኑ ትርጉም የሰጠ

በመሆኑ አመልካች የቤቱ ባለሀብት ሆኜ እያለ የሥር ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ ያቀረብኩትን መከራከሪያ በማለፍ ቤቱ የተገዛው በተጠሪ ገንዘብ በመሆኑ ቤቱ የተጠሪ ንብረት ነው በማለት የደረሰበት መደምደሚያና ይህን የሥር ፍርድ ቤቱን ውሳኔ ያጸናው የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡ ተጠሪ የውጭ ዜጋ ሆነው እያለ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት እንዲረከቡ መወሰኑ የፍ/ህ/ቁ 390/1 ድንጋጌን የጣሰ ነው ፤ ተሸከርካሪ በእኔ ገንዘብ ነው የተገዛው በሚል የተሸከርካሪው ባለቤት የሚኮንበት የህግ አግባብ የለም የተሰጠው ውሳኔ ስለልዩ ተንቀሳቃሽ ንብረት ባለሀብትነት ጥበቃ የወጡትን የአገሪቱን የህግ ማዕቀፎችና ህገመንግሰቱ ስለንበረት መብት የሰጠውን ዋስትና የጣሰ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት ተጠሪ ከላከላት ብር 3,500,000 ለአመልካች ሰጥቶ ቤቱ የተገዛው በብር 2,000,000 ብር ስለሆነ ቀሪው ብር 1,520,000 አመልካች አለመውሰዷን አላስረዳችም ለግል ጥቅሟ አውላለች ኪሳራ መክፈል አለባት ተብሎ በውሳኔው ላይ ከሰፈረ በኋላ፤ በተገላቢጦሽ ከቤቱ ሽያጭ የተረፈው ገንዘብ ብር 1,520,000 አመልካች ለተጠሪ ትመልስ በማለት የስር ፍ/ቤቱ ደረሰበት መደምደሚያ መሰረታዊ የህግ ስህተት የታየበት ነው፡፡

የቤት ቁሳቁሶቹ በአመልካች እጅ የሚገኙ እና የተገዙበት ደረሰኝም በአመልካች ስም የተገዙ መሆናቸውን በግልጽ ስለሚያረዱ በቤቱ ቁሳቁሶች ላይ አመልካች ከተጠሪ የተሻለ መብት እያለን የተጠሪ ናቸው ተብሎ መወሰኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1151፣ 1161፣ 1186 ፣ 1164 እና አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4(ሀ)(ለ)) ድነንጋጌዎች አንጻር የህግ ስህትት የተፈጸመበት ነው፡፡ አመልካች ኪሳራ ትክፈል ከተባልኩ ንብረቶቹን በአይነት አስረክቢ ልባል የምችልበት የህግ አግባብ የለም፡፡ ተጠሪ ክሱን ለማቅረብ የሚያስቸላቸው የክስ ምክንያት፣ መብትና ጥቅም፣ የላቸውም እንዲባልልኝ፣ ክሱን ለማቅረብ መብትና ጥቅም አላቸው ከተባለም ክሱ በይርጋ የታገደ ነው እንዲባልልኝ ፤ በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 10 የቤት ቁጥር አዲስ የከርታ ቁጥር ቦ10/43/9/11/49694/18781 የሆነው መኖሪያ ቤት እና የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 3-029086 ተሽከርካሪ አመልካች ለተጠሪ ሊያስረክቡ አይገባም እንዲባልልኝ፤ አመልካች ብር 1,5200,000.00 ተጠሪ ዕዳ የሌለባቸውና ዕምነት በሚያጎድል ሁኔታ የወሰዱት ገንዘብ ስለሌለ አመልካች ለተጠሪ ሊከፍሉ አይገባም እንዲባልልን፣ ወጪና ኪሳራ ብር 142,818 ለተጠሪ ሊከፍሉ አይገባም እንዲባልልኝ፣ ችሎቱ በከላይ የተጠየቁትን ዳኝነቶች የሚያልፍበት የህግ ምክንያት ካለውም አመልካች ለተጠሪ ተጠያቂ መሆን የሚገባን ኢትዮጵያ ውስጥ ገባ ለተባለው ዩሮ ብቻ ነው ተብሎ

ወጪና ኪሳራ የመጠበቅ መብታችን ተጠብቆ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ እና አስቀድሞ የተያዘው ጭብጥ ተሻሽሎ መመርመር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ሰበር ችሎቱ ቀድሞ የተያዘውን ጭብጥ በማሻሻል፣ 1ኛ/ የክርክሩ መነሻ የሆኑትን 72 ካሬ ላይ ያረፈ ባለ 3 ወለል መኖሪያ ቤት እና የሰሌዳ ቁጥር 2-አ.አ 88399 ወይም (ኮድ 3 B 29086

አ.አ) የሆነው ኮሮላ ተሽከርካሪ አመልካች በግዢ ውሉ በስማቸው ተዋውለው ገዝተውና በስማቸው አዘዋውረው በሚገኙበት፣ በሌላ የውል ሰነድ ለተጠሪ ጥቅም በተጠሪ ገንዘብ መገዛቱን የሚገልጽ በሌለበት ሁኔታ ተጠሪ ንብረቶቹ በገንዘባቸው የተገዙ መሆናቸውን አስረድተዋል በሚል አመልካች ለቀው እንዲያስረክቡ በስር ፍ/ቤቶች መወሰኑ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ.207885 ከሰጠው ገዢ ትርጉም አንጻር ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? እንዲሁም 2ኛ/ በተጠሪ ገንዘብ የተገዙ ግምታቸው ብር 76,846 የሆኑትን የቤት ዕቃዎችና ንብረቶች አመልካች ለተጠሪ እንዲያስረክቡ እና ከቤት ግዢ የተረፈ ገንዘብ ተብሎ ብር

1,520,000 አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍሉ በስር ፍ/ቤት የተወሰነው በአግባቡ ተጣርቶ መሆን አለመሆን ከመሰረታዊ የማስረጃ ምዘና መርህ አንጻር ለመመርመር ሲባል ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡

ተጠሪ ግንቦት 27 ቀን 2016 ዓ.ም በተጻፈ የሰጡት መልስ ይዘቱ ተጠሪ የከበቡሽ /ዲዲዮ ፋውንዴሽን በጉዲፈቻ ወላጅ አልባ ህጻናትን የማሳድግ ሲሆን ህጻናቱን ለዘላቂ መንከባከቢያ የሚሆን ቤት ለመግዛት ከአመልካች ጋር ተማክረን 110,000 (አንድ መቶ አስር ሺህ) ዩሮ ከምኖርበት ኔዘርላንድ ለማውጣት በተሰማራሁበት የበጎ አድራጎት ዘርፍ ያለኝን ፍቃድ አሳይቼ በኢትዮጵያ ለህጻናቱ ቤት ለመግዛት መሆኑ ተረጋግጦ በዲክላራሲዮን ተገልጾ ባስገባሁት ገንዘብ በአመልካች ስም መግዛቴ ሲታይ አመልካች ስመሀብቱ በስማቸው ስለተመዘገበ ብቻ የንበረቱ ባለቤት ሊሆኑ ስለማይችሉ አቤቱታቸው ውድቅ ይደረግ፡፡

አመልካች በወር 60,000 (ስልሳ ሺህ) ዩሮ ህጻናቱን ለመንከባብ ከተጠሪ ጋር በቀን 23/04/2005 ዓ.ም ውል ለመፈጸሙ የሚያረጋግጥ ማስረጃ የሚያረጋግጥ፣ ለህጻናቱ ቀለብ፣ የት/ቤት እና ሌሎች ወጪዎችን ለአመልካች በባንክ የምልክበት ደረሰኞች ከባንክ የቀረበ፣ የህጻናቱን እንክብካቤ በመገናኛ ዘዴ ለተጠሪ ይልኩ ስለመሆኑ በማስረጃ በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ በመሆኑ ንበረቶቹ የተገዛበት የገንዘብ ምንጭ፣ መንፈስ እና አላማ ተጠሪ ባለንበረት መሆናቸውን የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ የሚነቀፍበት አግባብ የለም፡፡ አመልካች ክርክር የተነሳበትን ቤት ለማፍራት የሚያስችል የገንዘብ አቅም ወይም ምንጭ አቅርበው ካለመከራከራቸው በላይ በስር ፍ/ቤት ቤቱ ከመገዛቱ በፊት የነበራቸው የባንክ ሂሳብ ዝርዝር እንዲቀርብ በማስረጃ ዝርዝራችን ጠይቀን  የተረጋገጠ ሲሆን በፍ/ብ/ህ/ቁ 1195 ስር የህግ ግምት ፍጹም ወይም መደምደሚያ ላይ የሚያስችል ማስረጃ አለመሆኑን በማንኛውም ማስረጃ ሊስተባበል እንደሚችል ከአንቀጽ 1196 አንጻር ይህንን የህግ ግምት ለማፍረስ በመቻላችን ውሳኔዎቹ

የህግም ሆነ የማስረጃ ምዘና ስህተት ስለሌለበት የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ይደረግልን፡፡ አንድ ሰው የንበረት ባለቤት ሊሆን የሚችለው በግል ጥረቱና ላቡ ሲያፈራ ብቻ ለመሆኑ መደንገጉ ማስረጃው ሊስተባበል የሚችል በመሆኑ አመልካች ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት ያቀረቡት ክርክር ነው፡፡ አመልካች የሚገዛው ቤት 3,500,000 (ሶስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ) ነው በማለት ከተጠሪ ተቀብላ 2,00,000 (ሁለት መቶ ሺህ) ገዝታ ቀሪውን 1,520,000 (አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሀያ ሺህ) ብር

ለግል ጥቅሟ በማዋላቸው ከሰነዶች ማረጋገጫ ውሉ ቀርቦ በተረጋገጠው መሰረት ውሳኔ የተሰጠ በመሆኑ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል፡፡ አመልካች አንክብካቤ የሚያስፈልጋቸውነ ልጆች ወደጎዳና እንዲወጡ በማድረግ የማይገባ ሀብት ለማፍራት የሚያደርጉት ጥረት ለሞራልና ለህሊና ተቃራኒ በመሆኑና በአጠቃላይ የህግ ድጋፍ ስሌለው የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ተደርጎ ወጪ እና ኪሳራ የማቅረብ መብታችን ተጠብቆ ይወሰንልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

መልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ግራቀኙ ክርክርና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፣ ለሰበር አቤ ቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ህጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ የቻልነው ፍሬ ጉዳዩን በማስረጃ የማጣራትና የመመዘን ስልጣን ያለው የስር ፍ/ቤት የቀረበለትን የሰነድ እና የሰው ማስረጃዎች የግራቀኙን የጽሁፍና የቃል ክርክር ሰምቶ የተከሳሽን የመጀመሪያ ደረጃ በብይን ውድቅ ካደረገ በኋላ ፣ በፍሬ ጉዳይ ላይ 1. በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 10 የቤት ቁጥር አዲስ የካርታ ቁጥሩ ቦሌ 10/43/9/11/49694/18781 የሆነው መኖሪያ ቤት ፣ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 2-88399 ወይም ኮድ -3-B 29086 አ.አ የሆነው ተሽከርካሪ የተገዛው በአመልካች ገንዘብ ነው? ወይስ አይደለም? አመልካች ቤቱ ከተገዛበት ገንዘብ ውጪ ብር 1,520,000 (አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሀያ ሺህ) ከተጠሪ ወስዳለች? ወይስ አልወሰደችም? እንዲሁም በክሱ ላይ የተዘረዘሩት የቤት ቁሳቁሶች በከሳሽ የተገዙ ናቸው? አይደሉም?የሚለውን ጭብጥ ለይቶ በመያዝ የግራቀኙን ምስክሮች ከሰማና በግራቀኙን የቀረቡትን ማስረጃዎች ከመረመረ በኋላ ከተቋማቱ በመጡት ምላሾች እና በቀረቡት ምስክሮች ንብረቶቹ በተጠሪ ከውጪ በገቡ እንዲሁም በባንክ በተላኩ እና ከተጠሪ ለአመልካች በተሰጠ ገንዘብ የተገዙ ስለመሆኑ በተሻለ ሁኔታ አስረድተዋል በማለት በአ/አ ከተማ ወረዳ 10 የቤ.ቁ አዲስ በካርታ ቁጥሩ ቦሌ 10/43/9/11/49694/18781 የሆነው መኖሪያ ቤት ፣ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 2-አ.አ 88399 ወይም ኮድ -3-B 29086 አ.አ በአመልካች ስም ተመዝግቦ የሚገኘው ተሽከርካሪ አመልካች ለተጠሪ ያስረክቡ፣ ከቤቱ ሽያጭ የተረፈውን ገንዘብ ብር 1520000 (አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሀያ ሺህ ብር) ክሱ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍሉ፣ ግመምታቸው 76,848 የሆነ የቤት ዕቃ ንብረቶች ተከሳሽ ለከሳሽ እንዲያስረክቡ ወጪና ኪሳራ እንዲከፍሉ በማለት የወሰነው በተጠሪ በኩል በአስረጂነት የተቆጠሩ ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ቃልን መሠረት በማድረግ በቀረቡት ምስክሮች ንብረቶቹ በተጠሪ ከውጪ በገቡ እንዲሁም በባንክ በተላኩ እና ከተጠሪ ለአመልካች በተሰጠ ገንዘብ የተገዙ ስለመሆኑ በተሻለ ሁኔታ አስረድተዋል የሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ ሲሆን፣ አከራካሪውን ቤትና ተሽከርካሪ አስመልክቶ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ስንመለከት የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነት በአስተዳደር ክፍል በተሰጠ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብት ምስክር ወረቀት እንደሚረጋገጥ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195/1 ሥር የሚደነግግ ሲሆን፣ ለዚህ ተቃራኒ ማስረጃ ማቅረብ

የሚቻለው ደግሞ የምስክር ወረቀቱ የተሰጠው ከደንብ ውጪ በሆነ አሠራር ወይም ይህን ለመስጠት ስልጣን በሌለው የአስተዳደር ክፍል እንደሆነ፣ የባለሀብትነት ምስክር ወረቀቱ የተሰጠው በማይረጋ ጽሁፍ

መሠረት የሆነ እንደሆነ ወይም ለከሳሹ መቃወሚያ ሊሆን በማይችል ጽሁፍ መሠረት እንደሆነ፣ ከሳሹ የማይንቀሳቀሰውን ንብረት ያገኘው የገዛው የባለሀብትነት የምስክር ወረቀት ከተሰጠ በኋላ መሆኑን ማስረዳት የቻለ እንደ ሆነ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1196 ከሀ-ሐ በተመለከቱት ንዑስ ፊደላት ላይ ተደንግጓል።

ከዚህም በተጨማሪ በጽሁፍ የተደረገ ውል በይዘቱ ውሉ ለጥቅሙ የተደረገለትን ሶስተኛ ወገን የማይገልጽ ከሆነ በውሉ ላይ በግልጽ ከተመለከቱት ከተዋዋዮች ሀሳብ ውጪ በመውጣት ተዋዋዩ ውሉን በስሙ የተዋዋለው ለራሱ ጥቅም ሳይሆን ለሌላ ሶስተኛ ወገን ጥቅም ነው በማለት በውሉ በግልጽ ከተመለከተው ተዋዋይ ውጪ ሌላ ሰው ተጠቃሚ እንዲሆን በማድረግ ፍርድ ቤቶች ውልን እንዲተረጉሙ ህግ ስለማይፈቅድ በእኔ ገንዘብ የተገዛ ቤት ነው በሚል በሌላ ሰው ስም የተገዛና የተመዘገበ ቤት ለማስለቀቅ የሚቀርብ ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 207885 አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል።

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የሥር ፍርድ ቤት ቤቱ የተገዛው በተጠሪው ገንዘብ ነው የሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰው የግራቀኙን ምስክሮች ከሰማና በግራቀኙን የቀረቡትን ማስረጃዎች ከመረመረ በኋላ ከተቋማቱ በመጡት ምላሾች እና በቀረቡት ምስክሮች ንብረቶቹ በተጠሪ ከውጪ በገቡ እንዲሁም በባንክ በተላኩ እና ከተጠሪ ለአመልካች በተሰጠ ገንዘብ የተገዙ ስለመሆኑ በተሻለ ሁኔታ አስረድተዋል በሚል ምክንያት ሲሆን፣ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነት ባለሀብትነት ላይ የሚቀርብ ተቃራኒ ማስረጃ ምን መሆን እንዳለበት ከላይ በተመለከተው ሁኔታ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1196 እና ንዑስ ፊደላት በተደነገገው መሠረት የቀረበለት ተቃራኒ ማስረጃ የሌለ ሲሆን አመልካች በስማቸው የገዙት ቤት ባለሀብት እንደሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195 መሠረት የህግ ግምት እንዳለ የሥር ፍርድ ቤቱ በውሳኔው ላይ ከገለጸ በኋላ፤ ለዚህ ተቃራኒ ማስረጃ ማቅረብ የሚቻለው የምስክር ወረቀቱ የተሰጠው ከደንብ ውጪ በሆነ አሠራር ወይም ይህን ለመስጠት ስልጣን በሌለው የአስተዳደር ክፍል እንደሆነ፣ የባለሀብትነት ምስክር ወረቀቱ የተሰጠው በማይረጋ ጽሁፍ መሠረት የሆነ እንደሆነ ወይም ለከሳሹ መቃወሚያ ሊሆን በማይችል ጽሁፍ መሠረት እንደሆነ፣ ከሳሹ የማይንቀሳቀሰውን ንብረት ያገኘው የገዛው የባለሀብትነት የምስክር ወረቀት ከተሰጠ በኋላ መሆኑን ማስረዳት የቻለ እንደ ሆነ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1196 ከሀ-ሐ በተመለከቱት ንዑስ ፊደላት ተደንግጎ እያለ ከእነዚህ በአንዱ ምክንያት የአመልካችዋ የቤት ባለሀብትነት የህግ ግምት ተቃራኒ ማስረጃ እንደቀረበበት የሥር ፍርድ ቤቱ ሳያረጋግጥና በውሳኔው ላይ ሳያመለክት አመልካችዋ በህግ የሚኖራቸውን የቤቱ ባለሀብትነት የህግ ግምት አግባብነት ባለው ማስረጃ ሳይስተባበል፤ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውንና በህግ ቅቡልነት የሌለውን የሰው ምስክሮቹን የምስክርነት ቃል ብቻ መሠረት በማድረግ አመልካችዋ የቤቱ ባለሀብት ስለመሆናቸው የሚወሰደውን የህግ ግምት ውጤት በማሳጣት ቤቱ የተገዛው በተጠሪው ገንዘብ ነው በማለት የተሰጠን የምስክርነት ቃል መሠረት

አድርጎ ቤቱን አመልካች ለተጠሪ እንዲያስረክቡ በማለት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ህግን መሠረት ያላደረገና የማስረጃ ምዘና ስህተት ያለበት ነው፡፡

ተሸከርካሪውን በተመለከተም ስመ ሀብቱ በአመልካችዋ ስም መሆኑ ግራ ቀኙን ያላከራከረ ጉዳይ ስለመሆኑ ከስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ይዘት መረዳት በመቻሉና ተሽከርካሪ ግዙፍነት ያለው ተንቀሳቃሽ ንብረት በመሆኑ ባለሀብትነት የሚረጋገጠው ውል ተዋውሎ በእጅ አድርጎ በመገኘት ስለመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1161 እና 1186 ድንጋጌዎች ጽንሰ ሃሳብ መረዳት የሚቻል ነው፡፡ የክርክሩ ምክንያት የሆነው ተሽከርካሪ በአመልካቿ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ከመሆኑ አንጻር የተሸከርካሪው ባለሀብት አመልካችዋ እንደሆኑ የህግ ግምት ይወሰዳል፡፡ በሥር ፍርድ ቤት የተሰሙት የተጠሪ ምስክሮች በሰጡት የምስክርነት ቃል ይህን የህግ ግምት የሚያስተባብል ባልሆነበት፤ የሥር ፍርድ ቤት በአመልካችዋ ስም ተመዝግቦ የሚገኘውን ተሽከራካሪ አመልካችዋ የገዙት በተጠሪው ገንዘብ ነው የሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ ተሸከርካሪውን አመልካች ለተጠሪ ታስረክብ በማለት የሰጠው ውሳኔም ህግን መሠረት ያላደረገና የማስረጃ ምዘና ስህተት ያለበት ነው፡፡

በመሆኑም ቤቱም ሆነ ተሸከርካሪው የተገዙት በአመልካችዋ ስም በተደረገ ውል መሆኑ ግራ ቀኙን ያላከራከረ ፍሬ ነገር ሆኖ እያለ አመልካችዋ ውሉን የተዋዋሉት ለራሳቸው ጥቅም ሳይሆን ለተጠሪው ጥቅም ነው በማለት ተዋዋይ ከሆኑት ከአመልካችዋ ውጪ የሆኑ ተጠሪውን ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ ውልን እንዲተረጉም ለሥር ፍርድ ቤቱ ህግ ሳይፈቅድለት ቤትና ተሸከርካሪው በተጠሪው ገንዘብ የተገዛ ነው በማለት የደረሰበት ድምዳሜ ከላይ የተጠቀሰውን የህግ ድንጋጌ እና የሰበር ሰሚ ችሎቱን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሚቃረን በመሆኑ ቤቱንና ተሸከርካሪውን አመልካች ለተጠሪ እንዲያስረክቡ በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡

የቤት ቁሳቁሶችን በተመለከተ ቁሳቁሶቹ በአመልካችዋ ስም የተገዙ ስለመሆናቸው በሥር ፍርድ ቤት በቀረቡ የግዢ ደረሰኞች መረጋገጡ ግራ ቀኙን ያላከራከረ ሲሆን፣ የሥር ፍርድ ቤቱ የእቃ ግዢ የተፈጸመባቸው ደረሰኞች ንብረቶቹ በአመልካችዋ ስም የተገዙ መሆናቸውን የሚያስረዱ ሆነው እያለ፣ በተጠሪው የቀረቡት ምስክሮች የሰጡትን ቃል ብቻ መሠረት በማድረግና በአመልካች ስም ንብረቶቹ የተገዙ መሆኑን ለሚያስረዱት ደረሰኞች ግምት ባለመስጠት፤ በአንጻሩ በተጠሪው ገንዘብ ለህጻናት ማሳደጊያ የተገዙ ንብረቶች ናቸው የሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ ንብረቶቹን አመልካች ለተጠሪ እንዲያስረክቡ በማለት የተሰጠው ውሳኔም የማስረጃ ምዘና ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡

አመልካችዋ ለቤት ግዢ ከአመልካች ብር 3,500,000 ተቀብለው ቤቱ በብር 2,000,000 ከተገዛ በኋላ የቀረውን ብር 1,520,000 አመልካች ለግል ጥቅሟ አውላለች በማለት፣ ቀሪ የተባለውን ገንዘብ ለተጠሪ ትመልስ ሲል የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በተመለከተ፣ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪው ለአመልካችዋ

ሰጠሁ የሚሉት ገንዘብ ወላጅ አልባ ለተባሉት ልጆች ጥቅም የዋለ ስለመሆኑ፣ ወይም በአመልካችዋ እጅ የቀረ ስለመሆኑ በሥር ፍርድ ቤት በተደረገ ክርክር በማስረጃ እንዲጣራ

አልተደረገም፡፡ በመሆኑም በተገቢው ሁኔታ ተጣርቶ የተጠቀሰውን ገንዘብ ብር 1,520,000 ከላይ በተጠቀሰው አግባብ ለማንኛው ጉዳይ እንደዋለ ሊጣራ ሲገባ የሥር ፍርድ ቤት ይህንን ሳይጣራ ገንዘቡን አመልካችዋ ለተጠሪ ያስረክቡ በማለት የተሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ሳይጣራ መሆኑን ተረድተናል፡፡

አከራካሪው ቤት፣ ተሽከርካሪ እና ግምታቸው 76,848/ሰባ ስድስት ሺ ስምንት መቶ አርባ ስምንት/ የሆነ የቤት ዕቃዎችን አመልካች ለተጠሪ ያስረክቡ፣ እንዲሁም ብር 1,520,000/ አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሃያ ሺ/ ክሱ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍሉ በሚል በሥር ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ከላይ በተመለከተው ምክንያት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሲሆን፣ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ከላይ በተመለከተው አግባብ የሥር ፍርድ ቤቱን ውሳኔ ሳያርም በመቅረት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 133829 በየካቲት 17 ቀን 2014 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ እና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 287342 ህዳር 15 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸው በመሆናቸው ውሳኔዎቹ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 ተሽረዋል ፡፡
2. በሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ የተመለከተውን ቤት፣ ተሽከራካሪ እና የቤት ዕቃዎች አመልካች ለተጠሪ ሊያስረክቡ አይገባም ብለናል፡፡
3. የሥር የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አከራካሪው ገንዘብ 1,520,000/አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሃያ ሺህ/ ወላጅ አልባ ለተባሉት ልጆች ጥቅም የዋለ ይሁን ወይም በአመልካችዋ እጅ የቀረ ስለመሆኑ በግራ ቀኙ የተቆጠሩ ምስክሮችን በመስማትና አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም አግባብነት ባለው አካልም ተጣርቶ እንዲቀርብለት በማድረግ ገንዘቡን አስመልክቶ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 343/1 መሠረት ጉዳዩ ለፌ/የመ/ደረጃ ፍ/ቤት ተመልሶለታል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻቻሉ፡፡
5. መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ::

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸምዓለማአየገለግልም!

ብ/ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መዝገብ ቁጥር -239892

ቀን - 08/02/2017

ዳኞች - ሽመክት አሰፋ

ገበየሁ ፈለቀ

አለማየሁ ሹናራ

ተናኜ ጥላሁን

ዘውዲቱ ታደሰ

አመልካች - ጌቱ ተፈራ አጠቃላይ አስመጪ - የቀረበ የለም

ተጠሪ - ጀሪ ማራኪ ኢንጅነሪንግ ኃ/የተ/የግ/ማ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው ለምርመራ ስለሆነ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በተጠሪ ላይ ያቀረበው ክስ ይዘት በአጭሩ የሞተር ብስክሌት መገጣጠሚያ ፋብሪካ ለማቋቋም ከተከሳሽ ጋር በ 06/04/2008 ኣ.ም የግንባታ ውል መዋዋላቸውን ተከሳሽ በ 250 ቀናት ውስጥ ግንባታውን አጠናቀው ለማስረከብ የውል ግዴታ ቢገባም በውሉ መሰረት በተቀመጠው ጊዜ ገደብ ውስጥ አጠናቀው አላስረከበም፡፡ ተከሳሽ በ 2 ወር ጊዜ ውስጥ ግንባታውን አጠናቀው እንዲያስረክቡ ተጨማሪ ውል ብናደርግም በ 14/09/2009 ኣ.ም አላጠናቀቀም፡፡ በተጨማሪ የሁለት ወር ተኩል ጊዜ ቢሰጥም አጠናቆ አላስረከበም፡፡ በዚህ መሰረት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በ 29/01/2010 ኢ.ም በተከሳሽ ጥፋት የግንባታ ውሉ እንዲቋረጥ ተደርጓል በመሆኑም ተከሳሽ ውሉን ባከለማክበሩ በከሳሽ ላይ የደረሰው ወጪና ኪሳራ

1. የቅድመ ክፍያ ተመላሽ ያልሆነ ቀሪ ገንዘብ ብር 241,566.07
2. ለስራው ከውጭ አገር የገቡ ማሽነሪዎች እና የተለያዩ ጥሬ እቃዎች በኢትዮጵያ ባህር መርከብ እና ሎጀስቲክስ አገልግሎት ድርጅት በተከራያቸው ኮንቴነሮች ውስጥ የሚገኙ በመሆኑ የኮንቴነሮች የኪራይ ክፍያ በዶላር 24,006.00 በብር 667,234 እንዲተካ
3. ግንባታው ለአንድ አመት ከዘጠኝ ወር በመዘግየቱ ምክንያት ፋብሪካው ወደ ስራ ያልገባ በመሆኑ ለፋብሪካው ወጪ የሆነውን የ 1 አመት ከ 9 ወር ብር 3,405,485.97 ኪሳራ እንዲከፍል
4. በተከሳሽ ሲሰራ በውሉ መሰረት በአግባቡ ያልተሰሩ ስራዎችን ለማስተካከል የሚያስፈልግ ወጪ ብር 1,070,859.51 እንዲተካ
5. አልሙኒየም ለመግጠም በቅድሚያ የተቀበለውን ብር 57,949.07 ከ 9% ወለድ ጋር እንዲከፍል
6. በውሉ መሰረት የበር እና የመስኮት ብረት አቅርቦ ለመግጠም ስምምነት ያደረገ ቢሆንም ለስራው የሚያስፈልገውን ብረት አላቀረበም፡፡ በልዩነት የወጣ ወጪ ብር 400,000.00 እንዲከፍል የሚል ነው፡፡

ተከሳሽ ለክሱ የሰጠው መልስ በአጭሩ በአንድ ወር ውስጥ ውሉን ከሳሽ ያቋረጠው በራሱ ጥፋት ነው፡፡ ከሳሽ የ 500,000.00 ብር ስራ ሲቀር ውሉን አቋርጧል፡፡ ግንባታው በውሉ መሰረት በጥራት ተሰርቶ የግንባታ ማጠናቀቂያ ላይ ሲደርስ ከሳሽ ውሉን አቋርጧል፡፡ ተከሳሽ ግንባታውን በውሉ መሰረት ላለመስራቱ ማስረጀ አላቀረበም፡፡ ግንባታው በየደረጃው እድገት ሲያሳይ እየታየና እየታረመ ከ 3/4 ኛ በላይ ግንባታ የተገነባ መሆኑ በሁለቱ ተዋዋይ ወገን ተቆጣጣሪ መሀንዲሶች ትዕዛዝ ክፍያ የተከፈለ ስለሆነ ግንባታው በጥራት የተሰራ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ተከሳሽ ጉድለት ቢኖር አስተካክል ተብሎ ይጠየቃል እንጂ ሳይጠየቅ ከሌላ 3ኛ ወገን ጋር አዲስ ደረጃውን ከፍ አድርጎ በማጋነን ሌላ የግንባታ ውል በመፈረም ይህን ወጪ ተከሳሽ እንዲተካ ሊጠይቅ አይገባም፡፡ ተከሳሽ የሰራው ስራ 85% በላይ መሆኑን በውሉ መሰረት ተከሳሽ ሰርቶ ያልተመለሰ ገንዘብ ብር 415,000.00 መሆኑን ስራው የዘገየው

1. የዲዛይኑ (ለውጥ) መሻሻል በማስፈለጉ
2. የተጨማሪ ግንባታ ስራዎች በመኖራቸው
3. ከሳሽ ክፍያውን በጊዜ አለመክፈሉ
4. ከሳሽ በውሉ መሰረት ጥሬ እቃ በጊዜ አለማቅረብ
5. የተከሳሽ ግንባታ መሳሪያዎች በመዘረፋቸው የቅድመ ክፍያ ብር 241,566.07 በተመለከተ በመዝገብ ቁጥር 199706 ተከሳሽ ከሳሽ ሆኖ በጠየቀው የመጨረሻ ክፍያ ጥያቄ ላይ ይህ ተቀናሽ ሆኖ አስቀድሞ ፍርድ የተሰጠበት ጉዳይ ስለሆነ ውድቅ እንዲደረግ፡፡ የኮንቴነር ኪራይ በተመለከተ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ግንባታው መጠናቀቅ ያለበት በነሀሴ ወር 2009 ኢ.ም ሆኖ እያለ ከሳሽ ውሉን መስከረም ወር 2010 ኢ.ም አቋርጧል፡፡ ይህ ኮንቴነር ለ 10 ወራት እስከ 14/09/2010 ኢ.ም ለቆመው ተከሳሽ ሊከፍል አይገባም፡፡

ከሳሽ የፋብሪካው ግንባታ መጠናቀቁን እርግጠኛ ሲሆን እቃዎች እንዲገቡ ማዘዝ ሲገባ በችኮላ በራሱ ጥፋት ያስገባ ስለሆነ ተከሳሽን ሊጠይቅ አይገባም፡፡ የብር 3,405,622 ጥያቄ በተመለከተ አሳማኝ ማስረጃ አልቀረበም፡፡ ከሳሽ ግንባታውን በራሱ ጥፋት አቋርጦ ኪሳራ መጠየቅ ተገቢነት የለውም፡፡ ከሳሽ ማስተካከያ ወጪ ብሎ ብር 1,070,859.00 የጠየቀው ለተቋረጠ ውል በመሆኑ አግባብነት የለውም፡፡ የአልሙኒየም ስራ ብር 57,949.07 እና የብረት ስራ ብር 400,000.00 በተመለከተ ተከሳሽ በተቀበለው ቅድሚያ ክፍያ አልሙኒየም ገዝቶ ለስራ ተዘጋጅቷል፡፡ ተከሳሽ ዋጋውን መመለስ አይችልም፡፡ ከሳሽ ራሱ ውሉን በማቋረጥ የተከሳሽን ድካም ከንቱ አድርጎታል፡፡ የብረት ስራን በተመለከተ ብረት የማቅረብ ግዴታ ያለበት ከሳሽ ነው፡፡ በዋናው ውል ላይ ብር 36,000.00 ሆኖ እያለ ብር 400,000.00 ግዥ አከናውኛለሁ ማለቱ ተቀባይነቱ የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ ግራ ቀኙ በችሎት ተገኝተው የቃል ክርክር አድርገዋል፡፡ የግራ ቀኙ ክስ፣ መልስ እና የቃል ክርክር ከተጠናቀቀ በኃላ ፍርድ ቤቱ

1. ውሉ የተቋረጠው በማን ጥፋት ነው?
2. በከሳሽ ላይ የደረሰ ጉዳት አለ?
3. በከሳሽ ላይ የደረሰ ጉዳት አለ ቢባል ምን አይነት ጉዳት ናቸው? መጠኑ ምን ያህል ነው?
4. ተከሳሽ የወሰደው ያልተመለሰ ቅድመ ክፍያ አለ ወይስ የለም? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ የግራ ቀኙን ምስክሮች ቃል ሰምቷል፡፡

የግራ ቀኙ ምስክሮች ተሰምቶ ከተጠናቀቀ በኃላ መዝገቡን መርምሮ ከሳሽና ተከሳሽ በመጀመሪያ 06/04/2008 ኢ.ም ያደረጉትን ውል በማሻሻል በግንቦት 14 ቀን 2009 ኢ.ም በድጋሚ ተዋውለዋል፡፡ በተሻሻለው ውል መሰረት ተከሳሽ ገንብቶ ለማስረከብ የተዋዋሉት ነሀሴ 2009 ኢ.ም ሲሆን ተከሳሽ ባለማስረከቡ ከሳሽ ውሉን ያቋረጠው መስከረም 2010 ኢ.ም በመሆኑ ተከሳሽ በውሉ መሰረት ባለማስረከቡ ውሉ የተቋረጠው በተከሳሽ ጥፋት ነው ተብሏል፡፡ ከሳሽ ውሉ ከተቋረጠ በኃላ ቀሪ ስራ እና በተከሳሽ ጥፋት የተበላሸ ስራ የሰራ ስለመሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ ስለሆነ የወጡ ወጪዎች ብር 1,070,859 ተከሳሽ ሊተካ ይገባል፡፡ የአልሙኒየም ገጠማ እና የብረት ስራ በተመለከተ ተከሳሽ የዋናውን ውል ግዴታ ያልተወጣ ስለሆነ ጉዳት ኪሳራውን ሊከፍል ይገባል፡፡ ስለዚህ ለአልሙኒየም ገጠማ ስራ ወስዶ ያልመለሰው ብር 57,949.00 እና የመስኮት ብረት ገጠማ የወጣ ተጨማሪ ወጪ ብር 400,000.00 እንዲከፍል፡፡ ተከሳሽ ግንባታውን አጠናቆ ባለማስረከቡ ለፋብሪካ የሚያስፈልጉ ማሽነሪዎች በኮንቴነር የተቀመጠበት ኪራይ ብር 667,234.00 እንዲከፍል፡፡ ስራውን አጠናቆ ባለማስረከቡ ከሳሽ ውሉን ካቋረጠበት ከመስከረም 2009 ኢ.ም ጀምሮ ይህ ክስ እስከተዘጋጀበት ግንቦት 14 ቀን 2010 ኢ.ም ለአንድ አመት ከዘጠኝ ወራት ወደ ምርት ሊገባ ስላልቻለ በከሳሽ ላይ የደረሰው ወለድ ብር 3,405,485.97 ተከሳሽ ሊከፍል አይገባም፡፡ ተከሳሽ ቅድመ ክፍያ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ተቀብሎ ያልመለሰውን ገንዘብ በተመለከተ ተከሳሽ ብር 241,566.07 እንዲመልስ በአጠቃላይ ተከሳሽ በከሳሽ ለደረሰ የጉዳት ኪሳራ ብር 2,437,608 (ሁለት ሚሊዮን አራት መቶ ሰላሳ ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ስምንት ብር) ፍርዱ ከተሰጠበት ከሀምሌ 02 ቀን 2012 አ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ፍርድ ላይ ተከሳሽ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ቅሬታ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ ተከሳሽ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበው ቅሬታ በአጭሩ ተጨማሪ ስራ ለመስራት የተዋዋልን ቢሆንም መጠኑን በተመለከተ ከመልስ ሰጪ ጋር አልወሰንም የስራው ብዛት ግንባታው በ 75 ቀናት እንዳይጠናቀቅ አድርጎታል፡፡ መልስ ሰጪ ክፍያ ለመፈፀም ፍቃደኛ አለመሆኑንና ማቴሪያል በወቅቱ ባለማቅረቡ ስራው እንዲዘገይ ማድረጉን በማስረጃ አስረድተናል፡፡ ይግባኝ ባይ የብር 258,000.00 ተጨማሪ ስራ መስራቱ ተረጋግጦ በመዝገብ ቁጥር 199706 መወሰኑ ለስራው መዘግየት መልስ ሰጪ መሆኑ የሚያረጋግጥ ስለሆነ ግንባታው ስለመዘግየቱ ብር 1,070,859.5 ተከሳሽ እንዲከፍል መወሰኑ ስህተት ነው፡፡ የውሉ አጠቃላይ ዋጋ ብር 4,800,000.00 ሲሆን 3/4 ተሰርቶ ቀሪ ስራ የብር 596,666.00 እንደሆነ በመዝገብ ቁጥር 199706 የተረጋገጠ ሲሆን ለቀሪ ስራ ክፍያውን ስላልተቀበልኩ ለቀሪ ስራ የወጣ ወጪ መልስ ሰጪ ሊጠይቅ አይችልም፡፡ የመጨረሻ ክፍያ ብር 1,207,830.00 ቢሆንም ቅድሚያ ክፍያ ብር 241,566.07 ተቀንሶ ብር 966,264.00 ስለሆነ መልስ ሰጪ በድጋሚ እንዲቀንስ ጠይቆ ፍርድ ቤቱ ይህን እንድከፍል መወሰኑ ስህተት ነው የሚል ነው፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የግንባታ ማስተካከያ ብር 1,070,859.00 እና ለፋብሪካው ስራ የተገዙ ማሽነሪዎችን የተቀመጡበትን ኮንቴነር ኪራይ ውጪ ብር 667,234.00 ተከሳሽ እንዲከፍል መወሰኑ በተመለከተ በውሉ መቋረጥ ጉዳትና ኪሳራ ደርሶብኛል የሚለው ከሳሽ ጉዳቱ በቀጥታ የውል መቋረጥ ውጤት መሆኑን የማስረዳት ግዴታ አለበት፡፡ ውሉ ከተቋረጠ በኃላ የተሰራው ስራ የጥራት ጉድለት አጋጥሞኛል በማለት መልስ ሰጪ (ከሳሽ) ከበደ የህንፃ ስራ ተቋራጭ ጋር ብር 1,070,859.51 ለመክፈል ግዴታ የገባ ሁለት ውሎች ለግንባታ የሚያስፈልጉ የግንባታ እቃዎችን የሚመለከት የግብአት አይነት ዝርዝርና ብዛት እንጂ ዋጋ የያዘ አይደለም፡፡ እነዚህ ጉድለቶች በተሻሻለው ውል መሰረት ቀሪ ግንባታውን አጠናቆ ባለማስረከቡ የመጡ ተጨማሪ ወጪን የሚመለከቱ ሳይሆኑ አስቀድሞ ይግባኝ ባይ (ተከሳሽ) ገንብቶና ተቀባይነት አግኝቶ ክፍያ የተፈፀመባቸው የስራ አካል ናቸው፡፡ ይህንን ለማስተካከል የግንባታው ጉድለት በገለልተኛ አካል ታይቶ የተረጋገጠበት ሁኔታ የለም ግንባታው ከተከናወነ በኃላ አሁን ባለበት ሁኔታ ማጣራት የሚቻል አይደለም፡፡ መልስ ሰጪ (ከሳሽ) ግንባታው ሳይጠናቀቅ በመቅረቱ ምክንያት የደረሰበት ጉዳት መኖሩን በተገቢው ማስረጃ ያላስረዳ ስለሆነ ከሁለተኛው ተቋራጭ ጋር በተደረገው ውል አስቀድሞ ለተሰራ ስራ ማስተካከያ ተብሎ በውሉ ዋጋው ስላሰፈረ ብቻ በመልስ ሰጪ (ከሳሽ) ላይ ይግባኝ ባይ (ተከሳሽ) ጥፋት የደረሰ ጉዳት እንደሆነ ተወስዶ ይግባኝ ባይ (ተከሳሽ) ብር 1,070,859.51 እንዲከፍል መወሰኑ ተገቢ አይደለም፡፡ ሁለተኛው ጭብጥ የግንባታ ውል መቋረጡን ተከትሎ በርና ብረት መስኮት ገጠማ በተመለከተ ከሳሽ (መልስ ሰጪ) ተጨማሪ ወጪ ብር 400,000.00 መክፈሉን የሚያሳይ ሰነድ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ማስረጃ ከማቅረብ ወጪ ለተከሳሽ (ይግባኝ ባይ) ለዚህ ስራ ስለመክፈሉ የሚያሳይ ማስረጃ አላቀረበም። ለተከሳሽ ሳይከፈል በልዩነት ብር 400,000.00 ተጨማሪ ክፍያ ከፍሏል ለማለት አይችልም ስለዚህ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አግባብነት የለውም። ቅድሚያ ክፍያ ብር 241,566.07 ሳንቲም ይግባኝ ባይ (ተከሳሽ) የተቀበለው ገንዘብ ከ 4ኛ ዙር ክፍያ ያልተመለሰ ስለሆነ የስር ፍርድ ቤት ቅድሚያ ክፍያ ብር 241,566.07 ይግባኝ ባይ (ተከሳሽ) ለመልስ ሰጪ (ከሳሽ) እንዲከፍል መወሰኑ በአግባብ ነው። የአሉሙኒየም ዋጋ ብር 57,947.00 ዋጋ ተከፍሎት ከተቆራረጠ በኃላ ለግንባታ ያልዋለ መሆኑ የተረጋገጠ ስለሆነ በስር ፍርድ ቤት ተከሳሽ እንዲከፍል መወሰኑ በአግባቡ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በማሻሻል ያልተሰሩ ስራዎች ለማስተካከል የሚያስፈልግ ወጪ የተባለው ብር 1,070,859.51 የኮንቴነር ዲመሬጅ ወጪ ብር 667,234 እና የበርና የብረት መስኮት ስራ ተጨማሪ ወጪ ብር 400,000.00 ለመልስ ሰጪ (ከሳሽ) ይግባኝ ባይ (ተከሳሽ) ሊከፈል አይገባም። ተከሳሽ ያልመለሰውን ቅድሚያ ክፍያ ብር 241,566.07 እና የአልሙኒየም ክፍያ ብር 57,949.07 በድምሩ ብር 299,515.14 (ሁለት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሺህ አምስት መቶ አስራ አምስት ብር ከአስራ አራት ሳንቲም) ከሀምሌ 02 ቀን 2012 አ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር ተከሳሽ እንዲከፍል በስር ፍርድ ቤት የተወሰነው የውሳኔ ክፍል ፀንቷል በማለት አሻሽሎ ወስኗል።

የአሁኑ ሰበር አቤቱታ የቀረበው አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት ነው። አመልካች በ 01/05/2015 አ.ም በ 05 ገፅ ፅፎ ያቀረበው ሰበር ቅሬታ ይዘት በአጭሩ የስራ ውሉ የተቋረጠው በተጠሪ ጥፋት መሆኑ በሁለቱ ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል። የስር ፍርድ ቤት የማስረጃ ምዘና መርህ የጣሰ ውሳኔ የሰጠ ስለሆነ ስህተት ነው። የስራ ውሉ በተጠሪው ጥፋት ሲቋረጥ አመልካች ያላለቁ ስራዎች ስለመኖራቸውና የተሰሩ ስራዎች ደግሞ ጉድለት ያለባቸው ስራዎችን ጉድለቶችን ለማስተካከልና ያላለቁ ስራዎችን ለማጠናቀቅ ለሌላ ተቋራጭ ለመስጠት የሚያስወጣ ወጪ በባለሞያ ተረጋግጧል። ተጠሪ ይህንን ሰነድ ማስረጃ የሚያስተባብል ማስረጃ አላቀረበም። የስር ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ውሳኔ የማስረጃ ምዘና መርህን ያልተከተለ ስለሆነ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው። ስራው በውሉ መሰረት ያልተጠናቀቀ በመሆኑ ለማሽነሪዎች ኪራይ ብር 667,234 አመልካች ያወጣውን ወጪ ተጠሪ ሊከፍል አይገባም ተብሎ የተወሰነው የማስረጃ ምዘና መርህ የጣሰ ስለሆነ ስህተት ነው። የግንባታ ውል በመቋረጡ ምክንያት ለበር መስኮት የአልሙኒየም እና የብረት ገጠማ የወጣ ወጪ ብር 400,000.00 ተጠሪ እንዲከፍል በከፍተኛ ፍርድ ቤት የተወሰነ ውሳኔ መሻሩ ስህተት ነው። ስለዚህ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ ተሽሮ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲፀናልኝ የሚል ነው።

አጣሪ ችሎት የውሉ መቋረጥ በተጠሪ ጥፋት ነው ከተባለ በአግባቡ ያልተሰሩ ስራዎች ጉዳት ወጪዎችን የኮንቴነሮች ዲመሬጅ እና የብረት መስኮትና የበር አልሙኒየም እቃዎች ወጪ ተጠሪ ኃላፊነት የለበትም የተባለበት አግባብነት ለማጣራት ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ የበኩሉን መልስ በ 21/06/2015 አ.ም በተፃፈ 04 ገፅ አቅርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል። ይዘቱ በአጭሩ ስራው 95% በላይ መስራቱ በአመልካችና ተጠሪ

አማካሪ መሀንዲስ ተረጋግጦ አመልካች ክፍያውን ከከፈለ በኃላ ስራውን ተረክቦ ለጉድለት ማስተካከያ ወጭ ብር 1,070,859 አውጥቻለሁ በማለት ለመጠየቅ አይችልም። ተጠሪ ቀሪ ክፍያ አለኝ ብሎ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 199706 ክስ አቅርቤ ገለልተኛ መሀንዲስ ተመድቦ አይቶ የተሰራውን ስራ በሙሉ አፅድቆ አመልካች ለተጠሪ ቀሪ ብር 369,603.00 እንዲከፍል እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር በመዝገብ ቁጥር 187223 በሆነ መዝገብ ፀድቆ ተወስኖ እያለ አመልካች ላልተሰራ ስራ እና ጉድለት ማስተካከያ ብር 1,070,859.00 እንዲከፍል መጠየቁ አግባብ አይደለም። የበርና መስኮት ወጪ ብር 400,000.00 በተመለከተ ስራው በተጠሪ ባለመሰራቱ ለእጅ ስራ ብር 36,000.00 ለመክፈል የተዋዋልነውን አመልካች አልከፈለም። ስለዚህ ከሌላ ከ 3ኛ ወገን ጋር የበርና የመስኮት ስራ ብር 400,000.00 በማድረግ የተዋዋለውን ተጠሪ የምከፍልበት ምክንያት የለም። በአጠቃላይ የስር የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማሻሻል የሰጠው ፍርድ በአግባቡ ስለሆነ እንዲያፀናልኝ በማለት መልስ ሰጥቷል። አመልካች የመልስ መልሱን በመጋቢት 7 ቀን 2015 ዓ.ም በተፃፈ 03 ገፅ ሰበር ቅሬታ በማጠናከር አቅርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ በተገለፀው መሰረት በመጠቃለሉ እኛም የግራ ቀኙ ክርክር እና የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በአጣሪ ችሎት ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ተጠሪ ስራውን አጠናቆ ባለመስጠቱ የስራ ውሉ የተቋረጠው በተጠሪ ጥፋት መሆኑ በተረጋገጠበት አመልካች ቀሪ ስራ በሌላ ተቋራጭ ለማሰራት የሚያስፈልግና ስራው ባለመሰራቱ ምክንያት ማሽነሪዎችን ለማስቀመጥ ለኮንቴነር ኪራይ የወጣ ወጪ እና በርና መስኮት ለማሰራት ለሌላ 3ኛ ወገን የሚከፈል ወጪ በአጠቃላይ ብር 1,070,859.51፣ ብር 400,000.00 እና ብር 667,234.00 ተጠሪ ለአመልካች ሊከፍል አይገባም ተብሎ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሻረው በአግባቡ መሆን አለመሆኑን በጭብጥነት በመያዝ እንደሚከተለው መርምረናል። የአመልካች ዳኝነት ጥያቄ ውሉ በተጠሪ ጥፋት የተቋረጠ ስለሆነ የተበላሸና ቀሪ ያልተሰሩ ስራዎች በሌላ ባለሞያ ለማስራት የሚወጣ ወጪ የወደብ ኪራይና ሌሎች ወጪዎች ተጠሪ እንዲከፍል የሚል ነው። ተጠሪ በሰጠው መልስ ስራው ከ 85% በላይ መስራቱን ገንዘቡም በአመልካችና ተጠሪ በሁለቱ ተዋዋይ መሀንዲሶች ተረጋግጦ የተከፈለ መሆኑ ስራው የዘገየው የዲዛይን ለውጥ በማስፈለጉ እንዲሻሻል በመደረጉ ተጨማሪ ግንባታ ስራዎች በመኖራቸው ከሳሽ ክፍያ በጊዜ ባለመክፈሉ ምክንያት እንደሆነ በመዘርዘር ክሱን ሙሉ በሙሉ ክዶ ተከራክሯል። ማስረጃ መመዘንና መመርመር ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ስራው ከ 85% በላይ መጠናቀቁ በአማካሪ መሀንዲስ ተረጋግጦ ተጠሪ ለተጨማሪ ስራ ያልተከፈለውን ገንዘብ አመልካች እንዲከፍል በሌላ መዝገብ ክስ አቅርቦ እንዲከፍል ያስወሰነ መሆኑን ክርክሩ ያስረዳል። አመልካች ተጠሪ የሰራውን ስራ ከተረከበ በኃላ የተበላሸ ስራ እና ተጨማሪ ስራ ነው ብሎ ከሌላ ባለሞያ ጋር ውል ፈፅሞ የውል ስምምነት ቢያቀርብም ለተጨማሪ ስራ የሚያስፈልገው ዋጋ ዝርዝር ሳይሆን የሚሰራው ስራ እና የማቴሪያል ዝርዝር በማቅረቡ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተቀባይነት ያለማግኘቱ በአግባቡ ሆኖ አግኝተናል። የወደብ ኪራይ ውጪን በተመለከተ ውሉ ከተቋረጠ በኃላ ለረጅም ጊዜ ኮንቴነሮች

ከወደብ ሳይነሱ መቆየታቸውና በኮንቴነር ውስጥ ያለውን ንብረት ከተጠሪ ውል አልመፈፀም ጋር ግንኙነት ያለው መሆኑ ባለመረጋገጡ ተጠሪ የወደብ ኪራይ ወጪ ሊከፈል አይገባም ማለቱ የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የብረት መስኮትና በር ገጠማ ወጪን በተመለከተ አመልካች ከሌላ ባለሞያ ጋር የተስማማበትን ስምምነት ቢያቀርብም ተጨማሪ ብር 400,000.00 የሚያስፈልግ መሆኑ በገለልተኛ ባለሞያ የተረጋገጠ ባለመሆኑ ተጠሪ ለአመልካች ብር 400,000.00 ሊከፈል አይገባም ተብሎ የተወሰነ ውሳኔ ከማስረጃ ምዘና መርህ አንፃር በአግባቡ ስለሆነ አልተቀበልነውም፡፡

ሲጠቃለል በአመልካችና ተጠሪ መካከል ያለው ውል በተጠሪ ምክንያት ቢቋረጥም በአመልካች መሀንዲስ የተሰራው ስራ ከ 85% በላይ መሆኑ ተረጋግጦ ክፍያ ለተጠሪ እንዲከፍል ታዞ ክፍያውን ከፍሎ ካሰናበት በኃላ የደረሰበትን ኪሳራ እንዲከፍል የጠየቀው አብዛኛው ጥያቄ ማስረጃ መመዘን ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት በገለልተኛ አካል የተረጋገጠ በመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰጠው ፍርድ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት ባለመገኘቱ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 194705 በቀን 04/02/2015 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት ስለሆነ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስነ ስርአት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9(1)(ሀ) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠ እግድ ካለ ተነስቷል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

የሰ/መ/ቁ :240451

7/2/2017

ዳኞች ሺመክት አሰፋ

ገበየሁ ፈለቀ

አለማየሁ ሹናራ

ተናኜ ጥላሁን

ዘውዲቱ ታደሰ

አመልካች፡ ሳይኖፒያ አስመጪና ላኪ ሃ/የተ//የግ/ማህበር አልቀረቡም

ተጠሪ፡ አቶ ጅሃድ መሃመድ አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሆኖ ተጠሪ ተከሳሽ ሲሆኑ አመልካች ደግሞ ከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡አመልካች በየካቲት 3 ቀን 2014 ዓ ም ያቀረቡት ክስ አመልካች የቡና ላኪ ድርጅት ሲሆን ተጠሪ ደግሞ ቡና አቅራቢ መሆናቸውን ፤ በዚህም መሰረት በአመልካችና በተጠሪ መካከል ቡና የማቅረብ ውል የነበራቸው በመሆኑ አመልካች 300 ኬሻ ወይም 18,300 ኪ ግ ቡና ተጠሪ እንዲያቀርቡላቸው ብር 3,000,000 (ሶስት ሚልየን ብር) በተጠሪ የባንክ ሂሳብ ገቢ

ማድረጋቸውን ገልጸው ከተላከው 300 ኬሻ ቡና ውስጥ አዲስ አበባ ውስጥ ርክክብ ሲደረግ ቡናው 18,020 ኪ. ግ ብቻ በመሆኑ የዚህ ሂሳብ ደግሞ ዊዝ ሆልዲንግ ታክስ ተቀንሶ ብር 3,220,280 (ሶስት ሚሊየን ሁለት መቶ ሃያ ሺ ሁለት መቶ ሰማኒያ ብር) ነው፡፡አመልካች ቀድሞ ከላከው 3,000,000 (ሶስት ሚሊየን ብር) የሚቀረውን ገንዘብ ተጨምሮ 300 ኬሻ ቡና ተጠሪ እንዲልኩ አዝገፔአቸው አንድ ላይ ሊከፈል ተስማምተን በ2 ጌዜ ክፍያ 3,300,000 (ሶስት ሚሊየን ሶስት መቶ ሺ ብር) በድጋሚ ገቢ አድርጌላቸዋለሁ፡፡

በአጠቃላይ አመልካች በሁለት ትእዛዞች በ3 ጌዜ ክፍያ በድምሩ ብር 6,300,000 (ስድስት ሚሊየን ሶስት መቶ ሺ ብር) ለተጠሪ መክፈሉን ገልጸዋል፡፡ተጠሪ መጀመሪያ ከላከው ቡና ውጭ ሌላ ቡና ሳይልኩ በመቅረታቸው በተደጋጋሚ ገንዘብ እንዲመልሱ ባቀረብኩላቸው ጥያቄ ብር 2,800,000 (ሁለት ሚሊየን ስምንት መቶ ሺ ብር) የመለሱ ሲሆን ሳይመለስ የቀረ ብር 252,680.60 (ሁለት መቶ አምሳ ሁለት ሺ ስድስት ምቶ ሰማኒያ ብር ከ60 ሳንቲም) እዳ ስላለባቸው እንዲመልሱና እና ተጠሪ የውል ግዴታ ያለባቸው በመሆኑ ውል ስላፈረሱ ቅጣት ብር 100,000 (መቶ ሺ ብር) እና ወለድ እንዲሁም ወጪ ኪሳራ ጭምር እንዲከፍሉ በማለት የቀረበ ነው፡፡

ተጠሪ ለክሱ መልስ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም በአጭሩ ውል መኖሩን አምነው በመጀመሪያ ዙር ያቀረብኩት ቡና 300 ኬሻ ቡና 18,300 ኪ. ግ ነው አመልካች ጅማ ከተማ ቀርቦ የተረከበ በመሆኑ የተረከብኩት ቡና 18,020 ኪ. ግ ነው የሚለው ሃሰት እና ተቀባይነት የለውም፡፡ውል ያፈረሰ የሚለውን በተመለከተ ተጠሪ ተጨማሪ አዘጋጅ የተባልኩትን 300 ኬሻ ቡና አዘጋጅቼ ብጠብቅም አመልካች ቀርቷል፡፡በተደጋጋሚ አመልካች እንዲወስድ ብጠይቀውም ብር የለኝም በማለት ሊረከብ ባለመቻሉ ውል ያፈረሰው አመልካች እራሱ ነው በማለት ተከራክሮዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ በአመልካች የተጠየቀው ብር 252,680.60 (ሁለት መቶ ሃምሳ ሁለት ሺ ስድስት መቶ ሰማኒያ ብር ከ 60 ሳንቲም) ወለድና ወጪ ኪሳራ ጨምሮ ተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል ፡፡300 ኬሻ ተብሎ የቀረበው ቡና በኪሎ ግራም ሲለካ 18,020 ኪ. ግ መሆኑ ተረጋግጦዋል ብሏል ፤ ለውሉ መፍረስ ተጠሪ ብር 100,000 (መቶ ሺ ብር) ቅጣት ሊከፍሉ ይገባል የሚለውን ክርክር በተመለከተ ግራ ቀኙ የገቡት ውል ተጠሪ ቡና በተገቢው ጌዜ መጠንና ጥራት እንዲያቀርቡ፤ አመልካች ደግሞ ክፍያ እንዲፈጽም እንጂ በልዩነት የተከፈለ ገንዘብ የሚመለስበትን ጌዜ ውሉ የጌዜ ገደብ አላስቀመጠም፡፡በልዩነት የተከፈለ ገንዘብም እንዲመለስለት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ማስጠንቀቂያ አልሰጠም ፤ ስለዚህም በልዩነት የሚከፈል ገንዘብ መኖሩ ብቻ ተጠሪ ውሉን አፍርሰዋል ተብሎ ቅጣት ክፈሉ ሊባል አይገባም በማለት ወሰነ፡፡በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር ተሰኝተው ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው፤የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገቡን መርምሮ ተጠሪን መጥራት ሳያስፈልግ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ አንቀፅ ፤ 337 መሰረት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

ይህ ፍ/ቤትም በስር ፍርድ ቤት የቅጣት ገንዘቡን በተመለከተ ማስጠንቀቂያ አልተሰጠም በማለት ሳይወሰን ማለፉ ተገቢ መሆን አለመሆን መልስ ሰጪ ባሉበት አግባብነቱን ለማጣራት እንደጭብጥ በመያዝ በአዋጅ ቁጥር፤ 1234/2013 አንቀጽ 28(3) መሰረት ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት በተደጋጋሚ ቢታዘዝም ባለመቅረባቸው ምክንያት በአማራጭነት በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ቢጠሩም ስላልቀረቡ ፍ/ቤቱ ተጠሪ መልስ መስጠት እንዳልፈለጉ በመቁጠር መልስ የመስጠት መብታቸውን አልፎታል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክር ይዘት አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም የቀረበውን ቅሬታ ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ፤በመዝገቡ ከተያዘው ጭብጥና እና ለጉዳዩ አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

አመልካች በውሉ ላይ ያለውን የመቀጮ ገንዘብ ተጠሪ እንዲከፍሉት የጠየቀው እኔ በገባሁት ውል መሰረት ገንዘብ ከፍዬ እያለ ተጠሪ ግን በገቡት ውል መሰረት ቡናውን መጀመርያ ካቀረቡት ውጪ አላቀረቡልኝም በማለት ነው፡፡ ተጠሪ ታድያ በውሉ መሰረት ቡናውን አሟልተው አቅርበዋል ወይ? ተሟልቶ ካልቀረበስ ለዚህ ተጠያቂው ማነው? የአመልካች ማስጠንቀቅያ አለመስጠትስ ተጠሪን ቅጣት እንዳይከፍሉ ያደርጋልወይ? የሚለው ነው ምላሽ የሚያስፈልገው፡፡ አመልካች ለጠየቀው ቡና ገንዘብ የከፈለ ስለመሆኑ ተጠሪ በባንክ የተላለፈላቸውን ገንዘብ ቡና ባለማቅረባቸው በአብዛኛው ገንዘቡን መልሰው የከፈሉ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡የቀረውንም እንዲከፍሉ ተወስኖባቸዋል፡፡

ለተጠሪ ገንዘቡ ዘግይቶ ደረሳቸው እንዳንል ከመዝገቡ እንደተረዳነው የመጀመርያው እና የሁለተኛው ክፍያ በሰኔ/2013 ሲሆን ሶስተኛው ክፍያም በሀምሌ10/2013 በባንክ የተደረገ መሆኑን ስለሚያሳይ አመልካች ገንዘብ አዘግይተው ቡና አልወሰዱላቸውም ለማለት ያዳግታል፡፡ ስለዚህ ቡናውን አሟልተው ያላቀረቡት ተጠሪ ናቸው፤የግዴታው አፈጻጸም ለመጓደሉም ተጠያቂው ተጠሪ ናቸው የሚል መደምደምያ ላይ አድርሶናል፡፡ተጠሪ በውል የተስማሙበትን የቅጣት ገንዘብ ብር

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

100000(አንድ መቶ ሺ) ሊከፍሉ ይገባል ወይስ አይገባም? የሚለውን በተመለከተ የፍ/ህ/ቁ/1889 ተዋዋዮች አንደኛው ወገን ግዴታውን ካልፈጸመ ወይም አጓደወሎ ወይም አዘግይቶ ከፈጸመ የሚከፈል መቀጮ አስቀድመው ሊዋዋሉ እንደሚችሉ ያስቀምጣል፡፡የመቀጮ ገንዘብ ሊጠየቅ የሚችለው ደግሞ ውሉ ባለመፈጸሙ ኪሳራ ሊጠየቅ በሚችልበት ግዜ ሁሉ እንደሆነ በፍ/ህ/ቁ1891 ላይ ተመልክቷል፡፡ስለዚህም ተጠሪ ለአመልካች ብር 100000(አንድ መቶ ሺ) ቅጣት ሊከፍሉ ይገባል ብለን ከዚህ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

- የፌደራል መጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 300140 በሰኔ 7ቀን 2014 ኢ.ም የወሰነውንና፤የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 295600 በጥቅምት 15 ቀን 2015ኢ.ም ያጸናውን ውሳኔ ሌላውን የውሳኔ ክፍል አጽንተን ተጠሪ ቅጣት ሊከፍሉ አይገባም ተብሎ የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል በመሻር ተጠሪ ለአመልካች ብር 100000(አንድ መቶ ሺ) ቅጣት ሊከፍሉ ይገባል ብለን በፌ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት አሻሽለን ወስነናል፡፡
- የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ ይቻቻሉ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፍ/ደ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ፡ 241349

7/2/2017

ዳኞች ሺመክት አሰፋ

አለማየሁ ሹናራ

ተናኜ ጥላሁን

ዘውዲቱ ታደሰ

ሀፊዝ አባጀማል

አመልካች፦ወ/ሮ መንበረ መንግስቱ - አልቀረቡም

ተጠሪ፦ወ/ሮ ነጃት ግዛው - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በፌ/ከ/ፍ/ቤት ሆኖ አመልካች ተከሳሽ ሲሆኑ ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ተጠሪ ሰኔ 3 ቀን 2011 ዓ ም ያቀረቡት ክስ በጉለሌ ክ/ከ ወረዳ 10 የቤት ቁጥር 1217 የሆነና በ130 ካሜ ቦታ ላይ ያረፈ ቤታቸውን አመልካች በብር 2100000 (ሁለት ሚልየን አንድ መቶ ሺ ብር) ሚያዝያ 07 ቀን 2011 ዓም በተደረገ የመኖሪያ ቤት ሽያጭ ውል ለመግዛት ተስማምተናል፡፡ከዚህ ሽያጭ ገንዘብ ውስጥ ብር 350,000 (ሶስት መቶ አምሳ ሺ ብር) በቤቱ ላይ ያለበት እዳ በመክፈል እግድ ለማስነሳት ክፍያ ከፍዬ በሰነዶች ማረጋገጫ በግንቦት 7 ቀን 2011 ዓ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ም ቀርበው በመዋዋል ቀሪ ክፍያ በሂደት እንዲቀበሉ ተስማምተናል፡፡ከዚህ ስምምነት በኋላ አመልካች ገንዘቡን በመውሰድ እዳቸውን ከከፈሉ በኋል የቤቱ ስመ ሃብት ለማዞር ፈቃደኛ ስላልሆኑ አመልካች ተገደው ውሉን እንዲፈጽሙ፡፡ይህ ካልሆነ የከፈልኩትን ገንዘብ ከነወለዱ እንዲሁም በውሉ ላይ ውል ላፈረሰ ወገን ከተቀመጠው ቅጣት ብር 500,000 (አምስት መቶ ሺ ብር) ጭምር አመልካች እንዲከፍሉ ተብሎ እንዲወሰን የቀረበ ነው፡፡

አመልካች በሰጡት መልስ ቤቱ የእኔ ብቻ አይደለም የሟች ባለቤቴም ጭምር ነው፡፡ከሟች ባለቤቴ 7 ልጆች ስለወለድኩ ከእነዚህ ልጆች አንዷ ከተጠሪ ጋር ተስማምታ ቤቱን እንድሸጥ ገፋፍታኝ እና ከተጠሪ ጋር አብረው በመሆን ታምሜ በተኛሁበት ውል ቢያስፈርሙኝም ሌሎች ልጆች ስላልተስማሙ ውሉ ሊፈጸም አይገባም በማለት ተከራከሩ፡፡የአመልካች 6 ልጆች በስር ፍ/ቤት የጣልቃ ገብ አቤቱታቸውን በማቅረብ በክርክሩ ቤት ላይ የአባታችን ድርሻ አለ፤ስለዚህ እኛ ሳንስማማ የተደረገ ሽያጭ ስለሆነ ውሉ ሊፈጸም አይችልም በማለት ተከራከሩ፡፡

የስር ፍ/ቤት የጣልቃ ገቦች አቤቱታ በማለፍ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል ከፍ/ህ/ቁ1723 አንጻር በውል አዋዋይ ፊት የተደረገ ውል ባለመሆኑ በህግ የሚጸና ውል አይደለም፡፡ይህ በመሆኑም ውሉ በፍ/ህ/ቁ፤1808(1) መሰረት ፈራሽ ውል በመሆኑ ግራ ቀኙ በፍ/ህ/ቁ፤1815 መሰረት ወደነበሩበት እንዲመለሱ፡፡አመልካች የወሰዱትን ብር 350,000 (ሶስት መቶ አምሳ ሺ ብር) ከነወለዱ ለተጠሪ እንዲከፍሉ፤የመቀጮ ገንዘብ ብር 500,000 (አምስት መቶ ሺ ብር) በተመለከተ ውሉ በህግ ፊት የማይጸና ስለሆነ ሊከፍሉ አይገባም በማለት ወሰነ፡፡ተጠሪ ይህን ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱ ውል በተዋዋይ ወገኖች ህግ መሆኑን በፍ/ህ/ቁ፤1731 ላይ በመደንገጉ አመልካች በውሉ ላይ የተቀመጠውን የገንዘብ መቀጮ ብር 500,000 (አምስት መቶ ሺ ብር) ሊከፍሉ ይገባል በማለት ወሰነ፡፡

ይህ ፍ/ቤትም ለሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነው ውሉ በህግ ፊት የማይጸና ከተባለ መቀጮ ይክፈል ተብሎ መወሰኑ የተፈጸመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖር ለመመርመር ያስቀርባል በማለት የግራ ቀኙ መልስ እና የመልስ መልስ በማስቀረብ አከራክሮዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክር ይዘት አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም የቀረበውን ክርክር፤ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ፤በዚህ መዝገብ ከተያዘው ጭብጥና እና ለጉዳዩ አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በግራቀኙ መካከል የተደረገው ውል የፈረሰው ወይም አይጸናም የተባለው በውል አዋዋይ ፊት አልተደረገም ተብሎ እንጂ ሌላ ጉድለት አለው አልተባለም፡፡ በውል አዋዋይ ፊት ያልተደረገ ቢሆንም አመልካች ውል አድርገው ብር 350000(ሶስት መቶ አምሳ ሺ) ከሚከፈላቸው ገንዘብ ውስጥ ቅድምያ መውሰዳቸው የተረጋገጠ ነው፡፡ አመልካችም ውሉን ላለመፈጸም ሌላ ምክንያት ቢያነሱም አልተዋዋልኩም ብለው በግልጽ የካዱ አደሉም፡፡ ውል ላፈረሰ ብር 500000(አምስት መቶ ሺ) ቅጣት ለመክፈል ደግሞ አመልካች ወደው ነው የተስማሙት፡፡ ስለዚህ የተዋዋሉት ውል በተዋዋይ ወገኖች መካከል እንደህግ ነው ተብሎ፤ውሉ ሊፈጸም ባለመቻሉና በመፍረሱ አመልካች የፍ/ህ/ቁ 1731 ተጠቅሶ በውሉ ላይ የተገለጸውን የቅጣት ገንዘብ እንዲከፍሉ ተብሎ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ሆኖ ስላገኘነው ከዚህ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

- የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 214615 በታህሳስ 20 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ጉድለት የሌለው ስለሆነ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት አጽንተነዋል፡፡
- የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ ይቻቻሉ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 241479

ጥቅምት 5 ቀን 2017 ዓ.ም

**ዳኞች** ፡-ሽመክት አሰፋ

ገበየሁ ፈለቀ

አለማየሁ ሹናራ

ተናኜ ጥላሁን

ዘውዲቱ ታደሰ

አመልካች፡- ጊዜው መድሐኒት የህክምና መሳሪያዎች ጅምላ አከፋፋይ - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ሀዋሳ ዩኒቨርስቲ - አልቀረቡም

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ሲሆን ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ጥር 26 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 258256 ጥር 18 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 222533 ሕዳር 2 ቀን 2014 ዓ.ም የተሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸው በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው መነሻነት ነው፡፡ ጉዳዩ የውል ይፈጸምልኝ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር አመልካች ከሳሽ እንዲሁም ተጠሪ ተከሳሽ ነበሩ፡፡

አመልካች ነሐሴ 29 ቀን 2012 ዓ.ም ጽፎ ያቀረበው ክስ ይዘት አመልካች ተጠሪ ግንቦት 9 ቀን 2011 ዓ.ም የራዲዮግራፊ ማሽን ለማቅረብ ባወጣው ጨረታ መሰረት ሙሉ በሙሉ አሟልቶ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የቀረበ ተወዳዳሪ ያልተገኘ በመሆኑ አመልካች ለማቅረብ የምችለውን የራዲዮግራፊ ማሽን ዝርዝር ሁኔታዎች ከመወዳደሪያ ሰነዱ ጋር አቅርቤ የኔ ከሌሎች ተወዳዳዎች ተሽሎ በመገኘቱ ጨረታውን አሸንፌ ማሽኑን በ 125 ቀናት ውስጥ ለማስረከብ፣ ከሳሽም ሳስረክበው ጠቅላላ ክፍያ 6,998,590.00 (ስድስት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ዘጠና ስምንት ሺህ አምስት መቶ ዘጠና ) ብር ለመክፈል ሰኔ 27 ቀን 2011 ዓ.ም ውል ገብተናል፡፡ በውላችን መሰረት ነሐሴ 16 ቀን 2011 ዓ.ም ማሽኑን ገጥሜ ክፍያውን እንዲፈጽምልኝ ብጠይቀውም ሊከፍለኝ ስላልቻለ ማስጠንቀቂያ ከሰጠሁበት ከመጋቢት 10 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ 11% ወለድና ወጪ ኪሳራ ጋር እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

ተጠሪ ህዳር 14 ቀን 2013 ዓ.ም በተጻፈ ባቀረቡት መልስ ይዘት አመልካች በውላችን መሰረት የኤክስሬይ ማሽን 2.00 (ሁለት ጡት) ፣ 32 ኪሎ ዋት፣ 43 ሳ.ሜ በ35 ሳ.ሜ ፍላት ፓኔል መቆጣጠሪያ እና መጠኑ 2 (ሁለት) መሆን ሲገባው ያቀረበው 1(አንድ) ብቻ ስለሆነ በውላችን መሰረት ግዴታውን ያልተወጣው ከሳሽ በመሆኑ የቀረበው ክስ ተገቢነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍሬ ጉዳዩን በማስረጃ የማጣራትና የመመዘን ስልጣን ያለው የስር ፍ/ቤት የቀረበለትን የሰነድ እና የሰው ማስረጃዎች የግራቀኙን የጽሁፍና የቃል ክርክር ሰምቶ ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት ተገቢነት አላቸው ያላቸውን ጭብጦችን ለይቶ በመያዝ የግራቀኙን ምስክሮች ከሰማና በግራቀኙን የቀረቡትን ማስረጃዎች ከመረመረ በኋላ በአመልካች የቀረበው የኤክሰሬይ ማሽን ከተጠሪ ጋር ከተዋዋሉት ውል አንጻር አንድ አይነት አለመሆኑን፣ የቀረበው ማሽን አጠቃላይ ሁኔታም ካልተተከለና ካልተገጣጠመ በስተቀር ለማወቅ የማይቻል መሆኑን በሰውና በሰነድ የቀረቡት ማስረጃዎች አረጋግጠዋል በማለትና ምንም እንኳን ተጠሪ ከአመልካች የቀረበውን ማሽን አስተዳደራዊ በሆነ መልኩ የተረከበው ቢሆንም አስተዳደራዊ በሆነ መልኩ መረከቡ ብቻውን ከሳሽ ከውሉ ውጪ ያቀረበውን ማሽን ወስዶ በውሉ ላይ የተመለከተውን 6,998,590.00 (ስድስት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ዘጠና ስምንት ሺህ አምስት መቶ ዘጠና ) እንዲከፍል የሚያስችል ግዴታ የለበትም የሚል ድምዳሜ ላይ ከደረሰ በኋላ፣ አመልካች ከውላቸው ውጪ ለተጠሪ ያቀረበውን ማሽን በራሱ ወጪ አንስቶ እንዲወስድ በማለት ነው የወሰነው፡፡ አመልካች ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የይግባኝ አቤቱታውን አቅርው ውሳኔው ሳይለወጥ ቀርቷል፡፡ በተጠሪው በኩል ቀርቦ የነበረውን የተከሳሽ ከሳሽ ክስም ውድቅ ያደረገው ሲሆን የተከሳሽ ከሳሽ ክሱ ላይ የተሰጠ ውሳኔን አስመልክቶ የቀረበ የሰበር አቤቱታ ባለመኖሩ የክርክሩን ምክንያት በዝርዝር መግለጽ አላስፈለገም፡፡

አመልካች ጥር 26 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፎ ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ይህን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ሲሆን ተጠሪ ባወጣው ጨረታ መስፈርቱን ሙሉ ለሙሉ አሟልቶ ያቀረበ ተወዳዳሪ ባለመኖሩ

አመልካች በሌሎች ተወዳዳሪዎች ከቀረበው የአቅርቦት መግለጫ የተሻለና፣ በተጠሪ ከተጠየው ተቀራራቢነት ያለውን በማቅረቤ አሸናፊ ሆኜ ማሽኑን ያቀረብኩና ውል የገባሁትም ጨረታው ይፋ ሲደረግ በተጠሪ በኩል ቀርቦ በነበረው ዝርዝር ሁኔታ መሰረት ሳይሆን፣ አቅርቤው በነበረው የአቅርቦት መግለጫ ዝርዝር መሰረት ስለመሆኑ አመልካች ባቀረብኳቸው ማስረጃዎች ተመልክቶ ባለበት አመልካች ማሽኑን ማቅረብ የነበረበት ተጠሪ አቅርቦት በነበረው ፍላጎት ዝርዝር መግለጫ ነው በሚል ውላችንን ያለአግባብ በመተርጎምና አዲስ ግዴታን በመፍጠር በውሉ ላይ በተመለከተው መሰረት ግዴታህን አልተወጣህም ሲል መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባ ነው፡፡ አመልካች ያቀረብኩትን ማሽን በራሴ ወጪ ባለሙያዎችን በማቅረብና ምቹ የሆነ ቦታም እንዲዘጋጅ ተደርጎ ማሽኑ ወደ 27 ቀናት ጊዜ ተወስዶ መገጠሙን፣ በገጠማ ወቅትም የተጠሪ የቴክኒክ ኮሚቴ ቼክሊስታቸውን ይዘው ማሽኑ ትክክል ስለመሆኑ የገቢ ደረሰኝ የተቆረጠልኝና ከጨረራ ባለስልጣን የጨረራ ልኬት አሰርቼ ለተጠሪ ውጤቱን ስለማቅረቤ በስር ፍ/ቤት ተረጋግጦ ባለበት ላይ ውሳኔ ማሳረፍ ሲገባው ማሽኑ ሊገጠም ይገባ የነበረው በአመልካች ዝርዝር ፍላጎት መሰረት ነው በሚል ክሱን ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡

ተጠሪ መ/ቤቱ በአመልካች ድርጅት በኩል የቀረበውን ማሽን በውሉ መሰረት ተሟልቶ ያልቀረበ በመሆኑ አልቀበልም ብሎ የመለሰበት ሁኔታ የለም፡፡ በውሉ መሰረትም እንደውሉ ተሟልቶ ካልቀረበ ወዲያው ለከሳሽ በመግለጽ መመለስ  በውሉ መሰረት አሟልቶ ማቅረብ መግለጽ እየተገባው የቀረበውን ኤክስሬይ ማሽን ለረዥም ጊዜ በራሱ ጉድለት ሳያሳውቅ እንዲሁም በአመልካች በኩል የቀረበውን የኤክስሬይ ማሽን በውላችን መሰረት መቅረቡን በማረጋገጥ ተጠሪ መ/ቤት የገቢ ደረሰኝ ጭምር የሰጠኝ ስለመሆኑ ተረጋግጦ ባለበት ሁኔታ ስር ከፍተኛ ፍ/ቤቱ ማሽኑ በውሉ መሰረት አልቀረበም በማለት የማሽኑ ዋጋ ሊከፈልህ አይገባም ከሚል ድምዳሜ መድረሱ ሊታረም የሚገባው የህግ ስህተት ስለሆነ የስር ፍ/ቤቱ እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው የሰጧቸው ውሳኔዎች ተሽረው አመልካች ድርጅት ያቀረብኩትን የኤክስሬይ ማሽን ዋጋ ብር 6,998,590.00 (ስድስት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ዘጠና ስምንት ሺህ አምስት መቶ ዘጠና ) ብር ከነህጋዊ ወለዱ እንዲከፍሉኝ ይወሰንልኝ ባማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ  አመልካች ከተጠሪ ጋር ባደረገው ውል አመልካች ለመወዳደሪያ ያቀረበው የተያዘው መስፈርት የውሉ አካል እንደሆነ በተገለጸበት ሁኔታ አመልካች ያቀረበው ዕቃ በውሉ መሰረት አይደለም የተባለበት ሁኔታ መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪ ግንቦት 07 ቀን 2016 ዓ.ም በተጻፈ የሰጠው መልስ ይዘቱ አመልካች በግዢ ውሉ እና የውሉ አካል በሆነው የፍላጎት እና የአቅርቦት መግለጫ መሰረት ማቅረብ የነበረበትን የኤክስሬይ ማሽን ሰነዱ ላይ ከፈረመ በኋላ ባለማቅረቡ ተጠሪ ስምንት የጉድለት አይነቶች እንዳሉበትና ያልተሟላ መሆኑን በስር ፍ/ቤት ክርክር ወቅት ያልተካደ በመሆኑ ጉድለት ላለበት ማሽን ክፍያ የምንከፍልበት አግባብ ስለሌለ አመልካች  የበኩሉን ግዴታ አልተወጣህም በማለት የስር የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው ተብሎ ሊጸና ይገባል፡፡  በተጠሪ በኩል የቀረበው

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የፍላጎት መግለጫ እና በአመልካች በኩል የቀረበው የአቅርቦት መግለጫ ሙሉ ተመሳሳይ ነው፡፡ ይህም በአመልካች እና በተጠሪ ተፈርሞ የውሉ አካል እንደሆነ በውሉ ላይ ተገልጾ እያለ በዚህ ውል መሰረት ሳያቀርቡ መቅረታቸው በስር ፍ/ቤት ተረጋግጦ እያለ እንዲሁም አመልካች በገለልተኛ አካል አስመርመሬያለሁ ከጨረራ ባለስልጣን ልኬት ሰርቻለሁ ቢልም ይህን በተመለከተ ውላችን ላይ የተገባ ግዴታ እና ስምምነት በሌለበት በስር ፍ/ቤት ክሱ ውድቅ መደረጉ ስህተት ነው በማለት ያቀረበው ክርክር ውድቅ ሊደረግ ይገባዋል፡፡ አመልካች ማሽኑን ያስረከበው በውሉ ላይ ያለውን መስፈርት ያሟላ መሆኑን አረጋግጦ አይደለም፡፡ ማሽኑ በባህሪው ከመገጠሙና ከመተከሉ በፊት የቴክኒክ ምርመራ ሊደረግለት የሚቻል ባለመሆኑ የገቢ ደረሰኝ ተቆረጠለት እንጂ ማሽኑ ከመተከሉና ከገጠማው በፊት ተመርምሮ በውሉ መሰረት ያለ አንዳች ጉድለት የቀረበ መሆኑን ተረጋግጦ አይደለም፤ አመልካች በዚህ ረገድ ለማሳሳት ያቀረበው አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል፡፡ በፌዴራል መንግስት መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 9 መሰረት ማንኛውም ግዢ የተፈጸመበት ዕቃ በተፈላጊ ባህሪያት ዝርዝር (ስፔስፍኬሽን) መሰረት ሲረጋገጥ የሚከፈል በመሆኑ ክፍያው ሊከፈል አይገባም ተብሎ በስር ከፍተኛ ፍ/ቤት መወሰኑ አግባብ ስለሆነ እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት አቤቱታውን ማጽደቁ አግባብ ነው ተብሎ የከሳሽ አቤቱታ ውድቅ ይደረግልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ግራቀኙ ክርክርና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፣ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ህጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ የቻልነው ፍሬ ጉዳዩን በማስረጃ የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው ክሱ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በግራ ቀኙ በኩል የቀረበለትን የጽሁፍና የቃል ክርክራቸውን ከሰማ በኋላ ለጉዳዩ እልባት ለመስጠጥ ተገቢነት አላቸው ያላቸውን ጭብጦችን ለይቶ በመያዝ የግራቀኙን ምስክሮች ከሰማና በግራቀኙን የቀረቡትን ማስረጃዎች ከመረመረ በኋላ ምንም እንኳን ተጠሪው ማሽኑን አስተዳደራዊ በሆነ መልኩ ከአመልካች የተረከበ ቢሆንም ፤ አስተዳደራዊ በሆነ መልኩ መረከቡ ብቻውን ከውሉ ውጪ አመልካቹ ያቀረበውን የኤክስሬይ ማሽን ተጠሪው ወስዶ በውሉ ላይ የተመለከተውን ገንዘብ እንዲከፍል የሚያስችል የውልም ሆነ የህግ መሠረት የለም የሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰ ሲሆን፣ በዚህ ድምዳሜ መነሻነትም አመልካቹ ከተጠሪ ጋር ካደረገው ውል ውጪ ያቀረበውን የኤክስሬይ ማሽን አመልካቹ በራሱ ወጪ አንስቶ እንዲወስድ በማለት ነው የወሰነው፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በመሠረቱ የሥር ፍርድ ቤት በፍርዱ ሀተታ ላይ በግራ ቀኙ መሐከል ሰኔ 27 ቀን 2011 ዓ/ም አመልካቹ የኤክስሬይ ማሽን ለማቅረብ፣ ተጠሪው ደግሞ ለመግዛት ውል መፈጸማቸውን ከዚህ ጋርም አጠቃላይ የውሉ ሁኔታዎች፣ ልዩ የውል ሁኔታዎች፣ የፍላጎት መግለጫ፣ የጨረታ መስከበሪያ ወረቀትና አቅራቢው ያቀረባቸው የዋጋ ዝርዝሮች፣ ግዢ ፈጻሚው አካል ለአቅራቢው ጨረታ ማሸነፉን ያሳወቀበት ሰነድ እና አቅራቢው ለመወዳደሪያ ያቀረበው የተያያዘ መስፈርትና ሌሎች ሰነዶችም የውሉ አካል መሆናቸውን ውል ያደረጉበት ሰነድ የሚያስረዳ ስለመሆኑ የገለጸ ሲሆን፣ አቅራቢ የሆነው አመልካቹ ለመወዳደሪያ ያቀረበው መስፈርትን የሥር ፍርድ ቤቱ የውሉ አካል መሆኑን አረጋግጦ እያለ፤ ይህንን የአመልካቹን የመወዳደሪያ ሰነድ በውሳኔው ላይ ግምት ሳይሰጥ አልፎታል፡፡

ይህ የውሉ አካል የተደረገ በውላቸው አንቀጽ 2/ረ ላይ የተመለከተው አቅራቢ የሆነው አመልካቹ ያቀረበው የመወዳደሪያ የተያያዘ መስፈርት የውሉ አካል በመሆኑና የተጠሪው ዋና መከራከሪያ የኤክስሬይ ማሽኑን አመላካቹ ማቅረብ የነበረበት፣ ተጠሪ ጨረታውን ባወጣበት የፍላጎት ዝርዝር መግለጫ መሠረት መሆን ነበረበት ከሚል በቀር፤ የኤክስሬይ ማሽኑ በአመልካቹ ባቀረበውና የጨረታው አሸናፊ በሆነበት መስፈርት መሠረት አልቀረበም የሚል መከራከሪያ በተጠሪ በኩል ያልቀረበ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት የውሉ አካል በተደረገው አመልካቹ ባቀረበው የመወዳደሪያ ሰነድ መሠረት የኤክስሬይ ማሽኑን ያቀረበ ሆነ እያለ የአመልካቹን የመወዳደሪያ ሰነድ እንደ ውሉ አካል ሳይቆጥር በማለፍ ተጠሪው ጨረታ ያወጣበትን የተጠሪውን የፍላጎት መግለጫ ብቻ መሰረት በማድረግ አመልካቹ ያቀረበው ማሽን በውላቸው ከተመለከተው ውጪ በመሆኑ በውሉ ላይ የተመለከተውን ገንዘብ ተጠሪው ሊከፍል አይገባም የሚለው የሥር ፍርድ ቤቱ ድምዳሜ እራሱ ያረጋገጠውን  አቅራቢው ለመወዳደሪያ ያቀረበው የተያያዘ መስፈርትና ሌሎች ሰነዶችም የውሉ አካል መሆናቸውን ከግምት ያላስገባ በመሆኑ አመልካቹ ለተጠሪ አቅርቦ እንዳስረከበውን የተረጋገጠውን የኤክስሬይ ማሽን ዋጋ ተጠሪው የመክፈል ግዴታ የለበትም በማለት አመልካች ማሽኑ በራሱ ወጪ አንስቶ እንዲወስድ በማለት የሰጠው ውሳኔ የማስረጃ ምዘና ጉድለት ያለበት በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመት ሲሆን፣ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ይህን ጉድለት ሳያርም በመቅረት የአመልካቹን የይግባኝ ቅሬታ መሰረዙ  መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

<u>ማስታወሻ</u>፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 258256 ጥር 18 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 222533 ሕዳር 2 ቀን 2014 ዓ.ም የተሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸው በመሆናቸው ፍርድና ትዕዛዙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 ተሽረዋል ፡፡
2. አመልካቹ የውሉ አካል በተደረገውና ጨረታውን ባሸነፈበት የመወዳደሪያ ሰነዱ ላይ በተመለከተው መስፈርት መሠረት አቅርቦ ተጠሪው የተረከበውን የራዲዮግራፊ/የኤክስሬይ ማሽን ዋጋ፣ ተጠሪው ከአመልካች ጋር ባደረገው ውል መሠረት ብር 6,998,590.00 (ስድስት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ዘጠና ስምንት ሺህ አምስት መቶ ዘጠና) ለአመልካች ይክፈል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ::

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የሰበር መ/ቁ 242355

ጥቅምት 06 ቀን 2017 ዓ/ም

ዳኞች:- ሽመክት አሰፋ

ገበየሁ ፈለቀ

ዓለማየሁ ሹናራ

ተናኘ ጥላሁን

ዘዉዲቱ ታደሰ

አመልካች ፡አቶ ሙሉቀን ጸጋው - አልቀረቡም

ተጠሪ፡ አቶ ሀይለየሱስ ዳኘ - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

የጉዳዩ መነሻ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 254483 ላይ በ25/02/2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት በሰጠው የአፈፃፀም ትዕዛዝ ላይ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 218325 አሻሽሎ የሰጠው ውሳኔ አግባብ ስላልሆነ ሊሻሻል ይገባል በማለት የሰበር አመልካች ቅሬታ በማቅረባቸዉ ነዉ፡፡ በስር ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች የፍርድ ባለመብት፣ ተጠሪ ደግሞ የፍርድ ባለ እዳ በመሆን የተከራከሩ ናቸዉ ፡፡

የጉዳዩ አጀማመር የሰበር አመልካች ተጠሪ የሸጡልኝን የሰሌዳ ቁጥሩ 03-79831 የሆነውን መኪና ስም እንዲያዛውሩ በተሰጠው ፍርድ መሠረት ይፈፅሙልኝ በሚል የተጀመረ ሲሆን ሲሆን ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ በሰጠው የአፈጻጸም ትእዛዝ የመኪናዉን የስም ዝዉዉር ለማድረግ በመኪናዉ ላይ ያለዉ የግብር ዕዳ ተጣሪቶ እንዲቀርብ ለግብር ሰብሳቢ ቅ/ጽ/ቤት ትዕዛዝ ሰቶ ከግብር ሰብሳቢ ቅ/ጽ/ቤት ሪፖረት እንዲቀርብለት ካደረገ በኋላ መኪናዉ የግብር እዳ እንዳለበት አረጋግጦ የመኪናዉ ሽያጭ ከመከናወኑ በፊት እስከ መስከረም 11/2011 ዓ/ም ድረስ ያለዉን የመኪና የግብር ዕዳ ተጠሪ እንዲከፍሉ የመኪናዉ ሽያጭ ተከናዉኖ የሰበር አመልካች መኪናዉን ከተረከቡ በኋላ ያለዉን የግብር እዳ ደግሞ የሰበር አመልካች ከፍለዉ የሰበር ተጠሪዉ የመኪናዉን ስመ ሀብት ወደ ሰበር አመልካች ያዙር ሲል ትእዛዝ ሰጥቷል ፡፡

አመልካች በዚህ ትእዛዝ ባለመስማማት ቅሬታቸዉን በይግባኝ ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ አመልካች ከመስከረም 11/2011 ዓ/ም በኋላ ማለትም ተሽከርካሪዉን ከተጠሪዉ ገዝተዉ ከተረከቡ በኋላ በተሽከርካሪዉ ካገኙት አገልግሎት በሰበሰቡት ገቢ ላይ የቫት ታክስን የመክፈል ግዴታ አለባቸዉ ፡፡ ነገር ግን የቫት ታክሱ ሊከፈል የሚችለዉ የተሽከርካሪዉ ስመ ሀብት ሲዞር በመሆኑ ይህ ግብር በጊዜዉ ባለመከፈሉ የሚመጣዉን ወለድ እና ቅጣት የሰበር ተጠሪዉ የተሽከርካሪዉን ሥመ ሀብት በጊዜዉ እንዲዞር ባለማድረጋቸዉ በራሳቸዉ ጥፋት ምክንያት የመጣ የግብር እዳ ስለሆነ የመክፈል ግዴታ ያለባቸዉ ተጠሪ ናቸዉ በማለት የፌዴራል ከፍተኛዉ ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ አሻሽሎ ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡

የሰበር አመልካች ቅሬታቸዉን ቀጥለዉ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበዋል ፡፡ አጭር ይዘቱም፡- አመልካች የቫት ተመዝጋቢ ባለመሆኔ ከደንበኞቼ ላይ የሰበሰብሁት ቫት በሌለበት ሁኔታ ወይም ተጠሪ ክርክር በተነሳበት መኪና አማካኝነት የሰበሰቡት ቫት በሌለበት ሁኔታ የቫት ታክስ ልከፍል አይገባም ፡፡ ተጠሪዉ የመኪናዉን ስመ ሀብት ወደ ሰበር አመልካች በወቅቱ ቢያስተላልፍ ኖሮ ዕዳዉ ሊኖር አይችልም ነበር ፡፡ ስለዚህ ያልተሰበሰበን ቫት ለዚያውም በተጠሪ ጥፋት መጣ ለተባለ ዕዳ አመልካችን ባለዕዳ የሚደርግ ውሳኔ መስጠት መሠረታዊ የህግ ስህተት ነው፡፡ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች የቫት ታክስ መክፈል ያለብህ በመኪናው ሰርተህ ከሰበሰብኸው (ካገኘኸው) ገቢ ላይ ነዉ ማለቱ ስህተት ነዉ ምክንያቱም የቫት ተመዝጋቢ ባለመሆኔ አይመለከተኝም እንጅ ባገኘኸው ገቢ መሠረት መክፈል አለብህ የምባል ቢሆን እንኳን ከእኔ የግብር ማህደር ላይ ያገኘሁት ገቢ ተጣርቶ እንዲገለፅ ተደርጎ እንጅ የገቢዎች ጽ/ቤት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ከተጠሪ የግብር ማህደር ላይ በግምት ሰርቶ በገለፀው ገቢ መሠረት መሆን የለበትም የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎቱ የሰበር ቅሬታዉን መርምሮ አፈጻጸሙ በፍርዱ መሰረት ነው ወይስ አይደለም የሚለውን መልስ ሰጪ ባሉበት አጣርቶ ለመመርመር ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኙ ክርክር አድርገዉበታል ፡፡

የሰበር ተጠሪዉ በሰጡት መልስ አመልካች በግልጽ አፈጻጸሙ ከፍርዱ ውጭ ነው የሚል ያቀረቡት ቅሬታ እና የጠየቁት ዳኝነት በሌለበት ሁኔታ ሰበር አጣሪ ችሎቱ አፈጻጸሙ በፍርዱ መሰረት ነው ወይስ አይደለም በሚል የያዘው ጭብጥ ከፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 182 አኳያ ባልተጠየቀ ዳኝነት ላይ የተያዘ ጭብጥ ስለሆነ የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በማጽናት ውሳኔ እንዲሰጥልኝ፡፡ ተጠሪ የቫት ተመዝጋቢ ስለሆንኩ እና መኪናውም የቫት ተመዝጋቢ በመሆኑ አመልካችም መኪናውን ሲገዙ ይሄን አውቀዉ እስከገዙ ድረስ እንዲሁም በዚህ መኪና ገቢ እስከሰበሰቡ ድረስ በመኪናው በሰሩበት ወቅት የመጣውን የቫት እዳ የመክፈል ግዴታ ያለባቸዉ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት የመኪናውን የቫት እዳ አመልካች እንዲከፍሉ የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ስለሆነ መጽናት የሚገባዉ ነዉ የሚል ይዘት ያለዉ ነዉ ፡፡

የሰበር አመልካችም የሰበር ቅሬታቸዉን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርበዉ ክርክሩ በዚሁ ተጠቃሏል፡፡ አጠቃላይ የክርክሩ አመጣጥ እና ይዘቱ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን እኛም ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ በስር ፍርድ ቤቶች ከተደረገዉ ክርክር የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እና ለጉዳዩ ተገቢነት ካለዉ ህግ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል ፡፡ እንደመረመርነዉም የሰበር አመልካች አከራካሪዉን መኪና ከሰበር ተጠሪዉ ተረክበዉ በመኪናዉ ስራ ሲሰሩበት የነበረ መሆኑን ክደዉ ያቀረቡት ክርክር የለም ፡፡ አጥብቀዉ የሚከራከሩት የቫት ተመዝጋቢ አይደለሁም የቫት ገንዘብም አልሰበሰብኩም እዳዉ የመጣዉ የሰበር ተጠሪዉ የመኪናዉን ስመ ሀብት በወቅቱ ባለማዛወራቸዉ ነዉ በእራቸዉ ጥፋት ነዉ በማለት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ይሁን እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ተጠሪዉ መኪናዉን በወቅቱ ባለማስረከባቸዉ የመጣዉን የግብር ዕዳ የቅጣት እና የወለድ ገንዘብ ሊከፍሉ ይገባል ብሎ ወስኖባቸዋል፡፡ ከዚያ ዉጪ መኪናዉ የቫት ተመዝጋቢ መሆኑ ያላከራከረ ስለሆነ የሰበር አመልካች መኪናዉን ከተጠሪ ተረክበዉ በመኪናዉ ለሰሩበት ጊዜ የቫት ክፍያዉን መሰብሰብ የሚችሉት በመኪናዉ አገልግሎት የሰጡት የሰበር አመልካች እንጅ የሰበር ተጠሪ በመኪናዉ አገልግሎት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ባልሰጡበት እና የባት ገንዘብ ከደንበኞች ላይ ለመሰብሰብ ዕድሉ ባልነበራቸዉ ወቅት ሁሉ ክፈሉ ሊባሉ የሚችሉት ህጋዊ ምክንያት የለም ፡፡ የሰበር አመልካች የከፍያዉን መጠን በተመለከተ በሰበር ቅሬታቸዉ ላይ ያነሱት ክርክር በስር ፍርድ ቤት በግልጽ ያልተነሳ እና ክርክር ያልቀረበበት ስለሆነ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 329 መሰረት ተቀባይነት ያለዉ አይደለም፡፡ ሲጠቃለል ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል

ዉሳኔ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በ/መ/ቁ 218325 ህዳር 07 ቀን 2015 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በ/መ/ቁ 254483 ጥቅምት 25 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉን ዉሳኔ በመሻሻል የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም ተብሎ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡

የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
## የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መ/ቁ 242695

ጥቅምት 08 ቀን 2017 ዓ/ም

ዳኞች:- ሽመክት አሰፋ

ገበየሁ ፈለቀ

ዓለማየሁ ሹናራ

ተናኘ ጥላሁን

ዘዉዲቱ ታደሰ

የሰበር አመልካቾች፡- 1. ወ/ሮ ፋናዬ ዶሼ ነጋሽ
2. አቶ ኃ/ማርያም አባተ በቀለ
} አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ አባይነሽ ዲማ ሰልፈቆ
2. ም/ሳጅን ተስፋዬ ዶሼ ነጋሽ
3. አቶ መለሰ ዶሼ ነጋሽ
} ጠበቃ አቶ መላኩ ገ/ስላሴ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች የካቲት 13 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈዉ ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 225883 ታሕሳስ 14 ቀን 2015 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸዉ ነው፡፡

ጉዳዩ የስጦታ ውል ይፍረስልን ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በስር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ነው፡፡ የስር ክርክሩ አመጣጥ በአጭሩ አመልካቾች ተከሳሾች ተጠሪዎች ደግሞ ከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል፡፡ በዚህም መሰረት ተጠሪዎች ጥቅምት 26 ቀን 2012 ዓ/ም ባቀረቡት ክስ አመልካቾች ከ1ኛ ተጠሪ ላይ እና ከሟች አቶ ዶሼ ነጋሽ ላይ በ1000 ካ.ሜ መሬት ላይ አርፎ የሚገኘውን ሰባት ክፍል ቤት በቀን 19/01/1985 ዓ/ም በስጦታ ተቀብለናል በማለት ይዘውት ይገኛሉ፡፡ ይሁን እንጅ ተያይዞ የቀረበውን የስጦታ ውል 1ኛተጠሪ ከባለቤቴ ጋር በመሆን አልሰጠሁኝም ትክክለኛ ሙሉ ስሜም ወ/ሮ አባይነሽ ድማም ተስፋዬ ሳይሆን ወ/ሮ አባይነሽ ዲማ ሰልፈቆ በመሆኑ በውሉ ላይ የተቀመጠው ስም እና ፊርማ የእኔ ባለመሆኑ በሀሰተኛ መንገድ ተዘጋጅቶ የቀረበ ሰነድ ነው፤ በቤቱ ላይ እስከ 2008 ዓ/ም ድረስ በ1ኛ ተጠሪ ሟች ባለቤት ስም ግብር ሲከፈልበት የቆየ ሲሆን ከ2009 እስከ 2011 ዓ/ም ድረስ ደግሞ በ1ኛ ተጠሪ ስም እየተከፈለበት ይገኛል፡፡ በይዞታው ላይ ተጨማሪ ሰባት ክፍል ቤት ሰርተናል፡፡ ስጦታ ውል መኖሩን ያወቅሁት ጥቅምት 2 ቀን 2009 ዓ/ም ነበር፡፡ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችም ስጦታ ውል መኖሩን የሰማነው ጥቅምት 2 ቀን 2009 ዓ/ም ሲሆን ይዞታው 1ኛ ተጠሪን ጨምሮ የወላጆቻችን በመሆኑ ወላጆቻችን በማገዝ እና በመርዳት በ2004 ዓ/ም ተጨማሪ ሰባት ክፍል ቤት ሰርተናል፡፡ ንብረቱን ከሟች አባታችን ድርሻ እንዳናገኝ ሆነ ተብሎ ከቅን ልቦና ውጭ የተዘጋጀ የሀሰተኛ ሰነድ እንጅ ትክክለኛ ስጦታ ውል አይደለም፡፡ በውሉ ላይ ወላጆቻችን አልፈረሙበትም፡፡ ስለሆነም መስከረም 19 ቀን 1985 ዓ/ም ተደረገ የተባለው ስጦታ ውል 1ኛ ተጠሪ የማላውቀውና ያልፈረምኩበት በመሆኑ በሀሰት የተዘጋጀው ስጦታ ውል እንዲፈርስልን በይዞታው ላይም በ2004 ዓም ሰባት ክፍል ቤት የሰራሁበት በመሆኑና ይህም ቤቱ በስጦታ አለመተላለፉን ስለሚያረጋግጥልን ውሉ ፈራሽ ነው ተብሎ ውሳኔ እንዲሰጥልን በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁን የሰበር አመልካቾች የመጀመሪያ መቃወሚያና መልስ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም ሟች አቶ ዶሼ ነጋሽ እና 1ኛ ተጠሪ የግል ንብረታቸው የሆነውን በ1000 ካ.ሜ ላይ ያረፈ ቤትና የእርሻ መሬት ማንም ሳያስገድዳቸው በነጻ ፈቃዳቸው በ19/01/1985 ዓ/ም በግልጽ ስጦታ ውል ሰጥተውናል፡፡ የውል ይፍረስልን ጥያቄ በፍ/ህ/ቁ. 1676 (1) እና 1845 መሰረት በ10 አመት ይርጋ እንዲሁም በ1ኛ ተጠሪ በመንፈስ ጫና ምክንያት ነዉ ቢባል ውሉን ለማፍረስ በ2 ዓመት ጊዜ ገደብ ያልቀረበ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኗል

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

እንዲሁም ተጠሪዎች ለ27 አመት ያህል ተጨማሪ ቤት ሰርተን እየተጠቀምንበት በምንገኘው ንብረት ላይ ክሱን ለማቅረብ የሚያስችላቸው መብትና ጥቅም የላቸውም ተብሎ መዝገቡ እንዲዘጋልን የሚል ሲሆን በፍሬ ጉዳዩ ላይ ደግሞ 1ኛ ተጠሪ እና ሟች አቶ ዶሼ ነጋሽ በ19/01/1985 ዓ/ም በ1000 ካ.ሜ ላይ ያረፈ አንድ ክፍል አሮጌ ሰርቪስ ቤት ከሰጡን በኋላ ተጨማሪ ከ13 ክፍሎች በላይ ሰርተን ለ25 አመት ያህል እስካሁን ድረስ እየኖርን እንገኛለን፤ ይህንን ከስለማድረጋችንም ከአሁን በፊት በመ/ቁ. 64703 እና 65820 በነበረን ክርክር ተረጋግጦልናል፡፡ ተጠሪዎች በይዞታው ላይ ምንም አይነት ተጨማሪ ቤት አልሰሩም፡፡ ከስጦታ ውሉ ጀምሮ ሟችም ሆነ 1ኛ ተጠሪ ሌላ ቤት ያላቸው በመሆኑ በዚህ ቤት ላይ ኖረው አያውቁም፡፡ 1ኛ አመልካች ከ2007 ዓ/ም ጀምሮ በይዞታው ላይ በስሜ ግብር እየከፈልሁበት እገኛለሁ፡፡ ሟች እና 1ኛ ተጠሪ ያደረጉትን ስጦታ ባለሙያ አማክረን በነጻ ፈቃዳቸው ምስክሮች ባሉበት ተጽፎ እና ተነቦ በፊርማቸው በማረጋገጥ የሰጡን በመሆኑ ውሉ ሊፈርስ አይገባም ፡፡ ተጠሪዎች በጥቅምት 2 ቀን 2009 ዓ/ም ውል መኖሩን አወቅን የሚሉት ከመጀመሪያው ጊዜ አንስቶ የሚያውቁ በመሆኑ ሀሰት ነው፡፡ ስለሆነም የተደረገው ሕጋዊ ስጦታ ውል በመሆኑ ሊፈርስ አይገባውም ተብሎ ውሳኔ ይሰጥልን በማለት መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልክ የቀረበለት የስር የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም አመልካቾች ያቀረቡትን የይርጋ መቃወሚያ በተመለከተ የግራ ቀኙን የሰው ማስረጃ ከሰማ በኃላ ተጠሪዎች የስጦታ ውሉን መኖሩን ያወቁት በ2009 ዓ/ም በመሆኑ የይርጋ ጊዜ ሊቆጠር የሚገባው ደግሞ ተጠሪዎቹ በመብታቸው መስራት ከቻሉበትና የስጦታ ውሉን መኖሩን ካወቁበት ጊዜ አንስቶ በመሆኑ ይህ ጊዜ ሲሰላ ደግሞ አስር አመት የማይሞላው በመሆኑ ክርክሩ በይርጋ አይታገድም በማለት በቀን 06/08/2012 ዓ/ም ብይን ሰጥቶ ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ ደግሞ የግራ ቀኙ ምስክሮች በመስማት የስጦታ ውል ጥብቅ የሆነ ስርዓትን የሚመለከት በመሆኑ እና በስጦታ ውሉ ላይ እማኝ የነበሩ ምስክሮች አንድ ቦታ ላይ ሆነው የስጦታ ውሉ ተነቦላቸው የፈረሙ ስለመሆኑ ስላልተረጋገጠ እና የአሁን 1ኛ ተጠሪ የስጦታ ውሉን ስለካዱ የስጦታ ውሉ ፈራሽ ነው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ቅሬታቸዉን በይግባኝ ለፌ/ከፍ/ፍ/ቤት አቅርበዉ ከፍተኛ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ ጉዳዩ አስቀድሞ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 64703 እና 65820 በተሰጡ ውሳኔዎች የመጨረሻ እልባት የተሰጠበት በመሆኑ በድጋሚ ሊታይ የሚገባዉ አይደለም በማለት የስር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠውን ፍርድ በመሻር ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የሰበር ተጠሪዎች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ ምንም እንኳን በመ/ቁ. 64703፣ 65802 እና ለይግባኙ መነሻ በሆነው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 89630 የነበሩት ተከራካሪዎች አንድ አይነት ቢሆንም በቀደሙት

መዝገቦች የነበረው የስር ነገር ጭብጥ ይዞታ ይለቀቅልኝ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ለይግባኙ መነሻ በሆነው በመ/ቁ. 89630 የተየዘው ጭብጥ ደግሞ የስጦታ ውል ይፍረስልኝ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ በመሆኑም የክርክሮቹ የስረ ነገር ክርክር እና ጭብጥ የተለያዩ ሆኖ ሳለ የስር የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በሌሎቹ በጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙ ባነሷቸዉ ክርክሮች መርምሮ መወሰን ሲገባው ተከራካሪ ወገኖቹ አንድ ስለሆኑ ብቻ መዝገቡ ከዚህ በፊት የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ ጉዳይ ነው ሲል የደረሰበት መደምደሚያ ተገቢነት የሌለዉ ነዉ በማለት ሽሮ ግራ ቀኙ የሚያቀርቧቸዉን ሌሎች ክርክሮች እና ማስረጃቸዉን መርምሮ ተገቢውን እንዲወስን ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343 (1) መሰረት ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መልሶለታል፡፡

በዚህ ዉሳኔ ባለመስማማት አመልካቾች የካቲት 13 ቀን 2015 ዓ/ም የተፃፈ የሰበር ቅሬታ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፡- ተጠሪዎች ከስጦታ ውሉ ጋር ተያይዞ ያነሱት ክርክር በመ/ቁ. 64703 እና 65820 የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ እና በድጋሜ የቀረበ ጉዳይ ነዉ፤ ክርክሩም የስጦታ ይፍረስልኝ ክርክር ስለሆነ በፍ/ብ/ህ/ቁ 2441 (1) እና የፌደራል ጠቅላይ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 23921፤ 29363፣105652 እና በተለዩ መዝገቦች በሰጣቸዉ አስገዳጅ የሆነ ህግ ትርጉሞች መሰረት በሁለት ዓመት ይርጋ የሚታገድ ነዉ የሚል ይዘት ያለዉ ነዉ፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ፌዴራል ከፍተኛዉ ፍርድ ቤት ጉዳዩ አስቀድሞ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 64703 እና 65820 በተሰጡ ውሳኔዎች የመጨረሻ እልባት የተሰጠበት በመሆኑ በድጋሜ ሊታይ የሚገባዉ አይደለም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5 መሰረት ዉድቅ የማድረጉን አግባብነትና ተያያዥ ነጥቦች ለማጣራት ያስቀርባል ብሎ ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት የጽሁፍ ክርክር አድርገዉበታል፡፡

የሰበር ተጠሪዎች ሰኔ 15 ቀን 2015 ዓ/ም የሰጡት መልስ ይዘት በአጭሩ፡- አስቀድሞ በመ/ቁ 64703 እና 65802 የቀረቡት ክርክሮች የይዞታ ይለቀቅልኝ ክርክሮች ናቸው፡፡ አሁን ይግባኝ በተባለበት በመቁ. 89630 የቀረበው ክርክር ደግሞ የስጦታ ውል ይፍረስልኝ ጥያቄ ነው፡፡ ፡፡ በመሆኑም ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍ/ቤት አስፈላጊ ከመሰለው ፍሬ ጉዳዩን ሊመረምር ይችል ካልሆነ በቀር ከላይ ያሉት ፍሬ ነገሮች በማስረጃና በህግ ክርክር ጠርተው በስር ፍ/ቤት በአግባቡ ተወስኖ እያለ በሌሎች መዝገቦች ተመሳሳይ ተከራካሪዎች በመቅረባቸው ብቻ ድጋሚ የቀረበ ክስ ነው ሲል የወሰነበት አግባብ ከህግ ውጭ ነው፡፡ የይርጋውም ጉዳይ ቢሆን ሊቆጠር የሚችለው በእርግጥም በአግባቡ በተደረገ የስጦታ ውልን በሚመለከት እንጂ ስሜ እንኳ የኔ ባልሆነበትና ምስክሮች ሲፈረም ባላዩበት፤ በየትኛውም ሁኔታ በማላውቀው የሃሰት ስጦታ ላይ ይርጋ ሊቆጠር አይገባም። ይርጋ ሊቆጠር ይገባዋል ቢባል እንኳ የስጦታ ውል የሚባል ነገር መኖሩን ያወቅኩት በ2/2/2009 ዓ.ም እንጂ ከዚያ በፊት በ1ኛ ተከሳሽ የተያዘ ባለቤቴ ግብር የሚከፍልበት የጋራ ሃብታችን

መሆኑን እንጂ ስለስጦታ ዉል  የማውቀው ነገር አልነበረም፡፡ በመሆኑም ስጦታ ተደርጓል መባሉን ካወቅኩበት ጊዜ ጀምሮ ሲሰላ 10 ዓመት የማያልፈው በመሆኑ በዚህ ረገድ በስር ፍ/ቤቶች በይርጋ አይታገድም በሚል የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው፡፡  ስለሆነም ፌ/ጠ/ፍ/ቤ/ ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመቁ. 225883 የሰጠዉ ዉሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ  በአመልካቾች የቀረበው የሰበር አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ የሚገባው ነው የሚል ይዘት ያለዉ ነዉ፡፡

የሰበር አመልካቾች የመልስ መልስ ያላቀረቡ ስለሆነ ክርክሩ በዚሁ የተጠቃለለ ነዉ፡፡ አጠቃላይ የክርክሩ አመጣጥ እና ይዘቱ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን እኛም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ፤ በስር ፍርድ ቤቶች ከተደረገዉ ክርክር ፤የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካለዉ ህግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነዉም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል የተያዘዉ ጭብጥ ፌዴራል ከፍተኛዉ ፍርድ ቤት ጉዳዩ አስቀድሞ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 64703 እና 65820 በተሰጡ ውሳኔዎች የመጨረሻ እልባት የተሰጠበት በመሆኑ በድጋሜ ሊታይ የሚገባዉ አይደለም በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5 መሰረት ዉድቅ የማድረጉን  አግባብነትና ተያያዥ ነጥቦችን ለማጣራት ተብሎ ነዉ፡፡ በመሰረቱ በፍ/ብ/ስ/ስህ/ቁ 5(1) መሰረት ማንኛዉም ፍርድ ቤት ክርክሩን ተቀብሎ የመጨረሻ ፍርድ ዉሳኔ ከሰጠ በኋላ ቀድሞ በፍርድ የተወሰነዉ ክርክር ስረ ነገር እና የተያዘዉ ጭብጥ አንድ ዓይነት ከሆነ በክርከሩ ላይ የነበሩት ወይም ከተከራካሪዎቹ መብት ያገኙ ሶስተኛ ወገኖች  በዚያዉ ነገር ሁለተኛ ክስ ወይም  ማናቸዉንም ዓይነት ሌላ ክርክር ሊቀርብባቸዉ አይችልም ፡፡ በዚህ መሰረት በስነ ስርዓት ህጉ መሟላት ካለባቸዉ ሁኔታዎች አንደኛዉ ቀድሞ ዉሳኔ የተሰጠበት እና አዲስ ክስ የቀረበበት ክርክር ስረ ነገር እና የተያዘዉ ጭብጥ አንድ ዓይነት መሆን ነዉ ፡፡ በተያዘዉ ጉዳይ አስቀድሞ የሰበር ተጠሪዎች አቅርበዉ የነበረዉ ይኸዉ አሁን ክርክር የቀረበበት ይዞታ እና ቤት አላግባብ በሰበር አመልካቾች የተያዘብን ስለሆነ ይለቀቅልኝ የሚል የነበረ ሲሆን የሰበር አመልካቾች በሰጦታ ያገኘነዉ ይዞታ እና ቤት ስለሆነ ልንለቅ አይገባም ብለዉ ተከራክረዉ ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 64703 ለሰበር አመልካቾች በስጦታ ተሰጥተዋል ወይስ አልተሰጡም የሚል ጭብጥ ይዞ እና ማስረጃ ሰምቶ በመመርመር አከራካሪዉ ይዞታ እና ቤት የሰበር አመልካቾች በስጦታ እና በዉርስ  ያገኙት ይዞታ ቤት ነዉ ብሎ አረጋግጦ ፍርድ እና ዉሳኔ ያሳረፈበት ነዉ ፡፡ ይህ ዉሳኔ በሰበር ተጠሪዎች ይግባኝ ተጠይቆበት የተሻረ አይደለም ፡፡ አሁንም የቀረበዉ ክርክር የዚሁ አስቀድሞ ፍርድ ያረፈበት ይዞታና ቤት የስጦታ ዉል ይፍረስልኝ ክርክር ነዉ ፡፡ የሚያዘዉ ጭብጥም የስጦታ ዉሉ ሊፈርስ ይገባል ወይስ አይገባም የሚል ነዉ፡፡ ይህ ጭብጥ ደግሞ አስቀድሞም ተይዞ ተጣርቶ የሰበር አመልካቾች በስጦታ እና በዉርስ ያገኙት ነዉ ተብሎ የመጨረሻ ፍርድ ያገኘ ነዉ፡፡ ክርክሮች የሚመሩት በፍትሐ ብሔር ስነ ስርዓት ህግ መሰረት ሲሆን የስነ ስርዓት ህጉ ዓላማም ጉዳዮች በአጭር ጊዜ እና በአነስተኛ ወጪ እልባት እንዲያገኙ ማድረግ እንጅ አንድ ተመሳሳይ ጉዳይ አርዕስት እየቀያየሩ ሁለት ሶስት ግዜ ክርክር እንዲካሄድ እና ተከራካሪ ወገኖች

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ባልተገባ መልኩ ለወጪ እንዲደረጉ፤ ግዜያቸዉን እንዲያባክኑ እና ጉዳይ እንዲጓተት ማድረግ አይደለም፡፡ ስለሆነም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 64703፣ 65802 እና ለሰበሩ መነሻ በሆነው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 89630 የነበሩት ተከራካሪዎች አንድ አይነት ቢሆንም በቀደሙት መዝገቦች የነበረው የስር ነገር ጭብጥ ይዞታ ይለቀቅልኝ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ለይግባኙ መነሻ በሆነው በመ/ቁ. 89630 የተየዘው ጭብጥ ደግሞ የስጦታ ውል ይፍረስልኝ ክርክርን የሚመለከት ነው በማለት የክርክሮቹ የስረ ነገር ክርክር እና የሚያዘዉ ጭብጥ የተለያዩ ናቸዉ ማለቱ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ መሻሩ አስቀድሞ የተደረገዉን የስረ ነገር ክርክር የተያዘዉን ጭብጥ እንዲሁም የተሰጠዉን የመጨረሻ ፍርድ፤ አሁን የቀረበዉን የስረ ነገር ክርክር እና ሊያዝ የሚገባዉን ጭብጥ እንዲሁም የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 5(1) ድንጋጌን በተገቢዉ ያላገናበ እና መስረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ የተገኘ ነዉ፡፡

በመሆኑም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል

<u>ዉሳኔ</u>

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 225883 ታህሳስ 14 ቀን 2015 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት ጉዳዩ በድጋሚ የቀረበ አይደለም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ተብሎ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348 (1) መሰረት ተሽሯል ፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 267883 ታህሳስ 21 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት ጉዳዩ አስቀድሞ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 64703 እና 65820 በተሰጡ ውሳኔዎች የመጨረሻ እልባት የተሰጠበት በመሆኑ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 5(1) መሰረት በድጋሜ ሊታይ የሚገባዉ አይደለም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢ ነዉ ተብሎ ጸንቷል፡፡

የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፍ/ደ

<u>ማስታወሻ</u>፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የሰበር መ/ቁ 243343

ጥቅምት 05 ቀን 2017 ዓ/ም

**ዳኞች:-** ሽመክት አሰፋ

ገበየሁ ፈለቀ

ዓለማየሁ ሹናራ

ተናኘ ጥላሁን

ዘዉዲቱ ታደሰ

አመልካቾች ፡-1ኛ/ የሱፍ ይመር -ሁሉም አልቀረቡም

2ኛ/ ይማም አህመድ

3ኛ/ ፋጡማ ዳውድ

4ኛ/ ኢብራሂም አደም ወራሽ ዑመር ኢብራሂም ወ/አማኑኤል

5ኛ/ ወ/ሮ አሥያ ካሣው

6ኛ/ አቶ መሐመድ የሱፍ ወራሽ ሠይድ ሙሄ

ተጠሪ፡- የሚች ወ/ሮ ፋጡማ አየለ ምትክ ወራሽ የሱፍ መሐመድ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍርድ**

መዝገቡ ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች የደቡብ ወሎ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በ/መ/ቁ.14302 እንዲሁም የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰ/መ/ቁ 0332283 የሰጠውን ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ይታረምልኝ በሚል ያቀረቡት ቅሬታ ነው።

ክርክሩ የዳግም ዳኝነት ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ጉዳዩ የተጀመረው የአሁን ተጠሪ በቀን 07/06/2011 ዓ.ም የተፃፈ ለደቡብ ወሎ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ ሲሆን ከፍ/ፍ/ቤቱ በይ/መ/ቁ 14302 በሆነው ከደቡብ ወ/ዞን/መ/አስ/ መምሪያ አከራካሪውን መሬት የማን እንደሆነ ካጣራ በኋላ የኩታበር ወ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 0113107 በሆነው ላይ የአሁን የሰበር አመልካቾች በተጠሪዋ ይዞታ ላይ ሁከት ፈጥረዋል ብሎ የሰጠውን ውሳኔ የሻረ ሲሆን እንዲሁም በዚህ ውሳኔ መነሻነትም የከፍ/ፍ/ቤቱ በ/ይ/መ/ቁ 22065 በሆነው የኩታበር ወ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 0115166 ላይ የአሁን አመልካቾች ለክርክር መነሻ የሆነውን መሬት ለአሁን ተጠሪ ለቀው እንዲስረክቡ በሚል የሰጠውን ውሳኔም ጉዳዩ በፍርድ ያለቀ ነው ብሎ ሽሮታል። ከፍ/ፍ/ቤቱ በይ/መ/ቁ 14302 ለውሳኔ መነሻ ያደረገው የደ/ወ/ዞን/ገ/መ/አስ/አጠ መምሪያ በቁጥር ደወአጥ/መ/03/156/114 በቀን 28/05/2006ዓ.ም ተጣርቷል ተብሎ የቀረበውን ማስረጃ ሲሆን የሰበር ተጠሪ ይህ ማስረጃ የዞኑ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቃም መምሪያ የቀበሌዉን እና የወረዳዉ መሬት አስተዳደር ሳያማክር እናማረጋገጫ ሳይቀበል የሰጠዉ የሀሰት ማስረጃ መሆኑን ስላረጋገጥሁ ዳግም ዳኝነት ይታይልኝ ብለዉ የጠየቁ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ቀበሌ እና ወረዳ ከዞን በታች እንጅ ከዞን በላይ ባለመሆናቸዉ ዞኑ የሰጠዉን ማስረጃ መሻር አይችሉም እንዲሁም ለዳግም ዳኝነት ይታይልኝ ጥያቄ ህጋዊ ምክንያት ሊሆን አይችልም ብሎ ጥያቄዉን ሳይቀበል ቀርቷል። የአሁን ተጠሪ በድጋሚ በክልሉ ርዕሰ መስተዳደርና የገጠር መሬት አስ/አጠ/ ቢሮ በኩል አጣሪ ቡድን ተልኮ የዞኑ ማስረጃ ስህተት መሆኑ ስለተረጋገጠ ድጋሚ ዳግም ዳኝነት ይታይልን ብለዉ በዚያዉ በይ/መ/ቁ 14302 ላይ ሲጠይቁ የአሁን አመልካቾ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ተጠሪ ያቀረቡት የዳግም ዳኝነት ጥያቄ በይርጋ የተገደበ ነው፣ ጉዳዩ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው የክልል አጣሪ ቡድኑ ጉዳዩን ያጣራው አመልካቾች ባልተገኙበት ሲሆን በሪፖርቱ ላይ እንደተገኘን መገለፁ ተገቢ አይደለም፤ የተጣራውም ለተጠሪ ቀረቤታ ባላቸው እና ለጉዳዩ እውቅና በሌላቸው ከቀጠናው ውጭ ባሉ ሰዎች አማካኝነት ነው፤ለክርክሩ መነሻ የሆነው የሣር መሬት በ1968 ዓ.ም ለአመልካቾች ተሰጥቶን የምንጠቀምበት እና በደርግ ዘመነ መንግስት ወደ አምራቾች ህብረት ስራ ማህበራት ተዛዉሮ ሲጠቀምበት ቆይቶ አምራች ሲፈርስ በ1984 ዓ.ም ወደ ነባር ባለይዞታዎች እንደሚመለስልን የተደረገ ነው፤ በመሆኑም በህጋዊ መንገድ ከ1968 ዓ.ም ጀምሮ የተደለደልንበትና ይዘን

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ

ስንጠቀምበት የቆየን መሬታችን ስለሆነ የቀረበው የዳግም ዳኝነት አቤቱታው ውድቅ ይደረግልን በማለት አቅርበዋል፡፡

ለሁለተኛ ግዜ የዳግም ዳኝነት ጥያቄ የቀረበለት የስር ደቡብ ወሎ ዞን ከፍ/ፍ/ቤትም የግራቀኙን ክርክር እና ማስረጃ በድጋሚ ከመረመረ በኂላ አስቀድሞ በዳግም ዳኝነት የሚስተናገድ አይደለም ያለዉን ዉሳኔ ተቀብሎ የክልሉ የመሬት አተቃቀም እና አስተዳደር ቢሮ የሰጠዉን ማስረጃ መሰረት አድርጎ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 6 መሰረት በዳግም ዳኝነት አይቶ ለተጠሪ ወስኗል፡፡

የሰበር አመልካቾች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቅሬታ ያቀረቡ ቢሆንም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአብላጫ ድምጽ በሰጠው ውሳኔ ተጠሪ የዳግም ዳኝነት አቤቱታ ከዚህ ቀደም ታይቶ ውድቅ የተደረገው ተጠሪ ተገኝ ያሉት አዲስ ማስረጃ ከቀበሌ መ/አስ/አጠ/ፅ/ቤት ባለሙያ በኩል ተጣርቶ የመጣ በመሆኑ ከፍ/ፍ/ቤቱ እንዲጣራ ያደረገው ደግሞ በዞን አካ/ጥ/መ/አስ/አጠ/ጽ/ቤት ባለሙያ በመሆኑ የቀበሌው ባለሙያ ማስረጃ የዞኑን ሊስተባብል አይችልም በሚል መነሻ ምክንያት መሆኑን ተጠሪ አሁን ያቀረቡት አዲስ የተገኘው ማስረጃ ደግሞ በክልሉ መ/አስ/አጠ/ቢሮ በኩል የቀረበ ሲሆን ይህ ማስረጃ የዞን መ/አስ/አጠ/ መመሪያ ባለሙያ የሰጠው ማስረጃ ሀሰተኛ መሆኑን የሚያሳይ ስለሆነ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በድጋሚ ዳግም ዳኝነት አይቶ መወሰኑ ተገቢ ነዉ በማለት አጽንቷል፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሳኔ ላይ ሲሆን ይዘቱ በአጭሩ ፡በክልሉ መስተዳድር የተሰየመው የገጠር መሬት ቢሮ አጣሪ ኮሚቴ የተለየ ማስረጃ አልሰጠም ያቀረበው ጥር 28 ቀን 2006 ዓ/ም የደ/ወ/ዞን አካ/ጥ/መ/ አስ/ የሰጡት ማረጋገጫ በሀሰት ተዘጋጅቶ የቀረበ ነው በሚል ያንኑ ሰነድ መነሻ አድርጎ ያጣራዉን ነዉ፡፡ ቀደምሲል የተደረገው ክርክር ጭብጥ ፣የቀረበው ማስረጃ ሆነ ተከራካሪዎች ተመሣሣይ ሆነው ሳለ የከ/ፍ/ቤቱ ያለበቂ ምክንያት አስቀድሞ በፍርድ አላለቀም ማለቱ ስህተት ነዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ሰበር ሰሚ ችሎትም ይህንን ማጽናቱ አላግባብ ነዉ የሚል ይዘት ያለዉ ነዉ፡፡

የሰበር ችሎቱም ለክርክር ምክንያት የሆነው ይዞታ በሀሰተኛ ማስረጃ የተወሰነ ነው በሚል ተጠሪ ባቀረበው አቤቱታ መነሻ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በስረ ነገሩ ላይ ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ በሰጠው ውሳኔ ላይ ቀጥታ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ቀርቦ መታየቱ ከፍ/ብ/ስ/ህግ ቁጥር 6 አተገባበር እና ከዚህ ጋር በተያያዘ ይዞታ ለሰበር ሰሚ ችሎት በተለያዩ መዝገቦች ከሰጠው ገዥ

ውሳኔ አኳያ ክርክሩ የተመራበት ስርአት ላይ የተፈጸመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አጣርቶ ለመመርመር ሲባል ያስቀርባል ብሎ ግራ ቀኙ ቀርበዉ ክርክር አድርገዉበታል፡፡

ተጠሪ ቀርበው የሰጡት መልስ ይዘት በአጭሩ፡- በዳግም ዳኝነት ዉሳኔ ላይ ይግባኝ ለማቅረብ አይቻልም በማለት ስነ ስርአት ህጉ የሚደነግግ ከመሆኑ በተጨማሪ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ቀደም ሲል በሰበር በመዝገብ ቁጥር 42871 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠበት ስለሆነ የአመልካቾች ቅሬታ በቀጥታ ለሰበር ቀርቦ መታየቱ ህግን መሰረት ያደረገ እንጂ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም፤ ለዚህ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ሃሰተኛ ማስረጃን መሰረት ተደርጎ በደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ዉሳኔ ሊሰጥ የቻለው በሥር ኩታበር ወረዳ ፍርድ ቤት ግራቀኛችን ክርክር አድርገን በተሰጠ ውሳኔ ላይ የአሁን አመልካቾች ቅር ተሰኝተው ለደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው የደ/ወሎ ዞን ከፍ/ፍ/ቤትም ክርክር ያስነሳውን ይዞታ የማን ነው የሚለውን ፍሬ ነገር የደ/ወሎ ዞን ገጠር መሬት አስ/መምሪያ አጣርቶ ማስረጃ እንዲልክ ትዕዛዝ ሰጥቶ ከደቡብ ወሎ ዞን ገጠር መሬት አስተዳደር/አጠቃቀም መምሪያ የተላከውን ሃሰተኛ ማስረጃ መሰረት አድርጎ የስር ወረዳ ፍርድ ቤትን ዉሳኔ መሻሩን፤ ይህ የዳግም ዳኝነት ጥያቄ የቀረበበት ዉሳኔ በይግባኝ ወደ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአሁን አመልካቾች ይግባኝ ተብሎ የመጣ መሆኑን በዚህ የዳግም ዳኝነት ዉሳኔ ላይ የአሁን አመልካቾች ይግባኝ መጠየቅ ነበረባቸው የሚባል ከሆነ ለአመልካቾች ለሁለተኛ ጊዜ ይግባኝ እንዲሉ መፍቀድ ስለሆነ ስነ ስርዓታዊ ያለመሆኑን ፤ይግባኙ በቀጥታ ለሰበር ሰሚ ችሎት ሊቀርብ አይገባም በማለት ቅሬታ ባላቀረቡበት ሁኔታ በዚህ ችሎት ባልተጠየቀ ዳኝነት የተያዘው ጭብጥ ሥነ ሥርዓታዊ አለመሆኑን ጠቅሰዉ የሰበር አቤቱታዉ ውድቅ መደረግ ያለበት መሆኑን ፤ እንዲሁም በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ/ቁጥር 6 ላይ የተዘረዘሩ መስፈርቶችን አሟልቶ በዳግም ዳኝነት ታይቶ የተሰጠው ዉሳኔ ለሰበር መቅረቡ ህግን መሰረት የደረገ እንጂ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ውሳኔ አይደለም በማለት የስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ እንዲፀናልኝ የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡

አመልካችም የሰበር ቅሬታቸዉን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርበው ክርክሩ በዚሁ ተጠቃሏል፡፡

አጠቃላይ የክርክሩ አመጣጥ እና ይዘቱ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን እኛም ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ በስር ፍርድ ቤቶች ከተደረገዉ ክርክር የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እና ለጉዳዩ ተገቢነት ካለዉ ህግ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል ፡፡ እንደመረመርነዉም

በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 6(1) ላይ ዳግም ዳኝነት ሊታይ የሚችለው የተሠጠው ፍርድ በሀሰት የተዘጋጀ ሠነድ ወይም ሀሰተኛ የምስክርነት ቃልን ወይም መደለያን ወይም ወንጀል ጠቀስ የሆነ ተግባርን መሠረት ያደረገ ከሆነ፣ አመልካቹ በክርክሩ ሂደት ተገቢው ትጋት አድርጎ ለማወቅ ያልቻለ መሆኑን ካሳየ እና የተፈጸመው ተግባር ቢታወቅ ኖሮ ፍርዱን ለመለወጥ ወይም ለማሻሻል በቂ ምክንያት ሊሆን የሚችል ሆኖ ሲገኝ መሆኑ ተመልክቷል ፡፡

በሌላም በኩል በ/ፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 6(2) የድንጋጌ ሙሉ ይዘትና መንፈስ የሚያሳየው የመጨረሻው ፍርድ ከተሰጠ በሁዋላ ሀሰተኛ ሰነድ ወይም ሀሰተኛ የምስክርነት ቃል ወይም መደለያ እንደተደረገና አቤት ባዮም ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት አስፈላጊውን ትጋት አድርጎ ለማወቅ ያለመቻሉን በሚገባ ለማስረዳት የሚችል የሆነ እንደሆነ ነዉ፡፡ ስለሆነም የዳግም ዳኝነት ጥያቄ የቀረበለት ፍርድ ቤት ለውሳኔው መሰረት የሆነው ሰነድ ወይም ማስረጃ ሐሰተኛ መሆኑን ብቻ ሳይሆን በህጉ ከላይ የተመለከቱት መመዘዎችን መሟላቱን አቤቱታ አቅራቢው ሊያረጋገጥ የሚገባ መሆኑን መገንዝብ ይገባል፡፡ በአሁኑ ጉዳይ የስር ፍርድ ቤት በዳግም ዳኝነት ለማየት መሰረት ያደረገዉ ማስረጃ ከክልል ገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም ቢሮ የቀረበ ማስረጃን ሲሆን ይህ ማስረጃ ፍርዱ ሲሰጥ ያልነበረ ለፍርዱም ምክንያት ያልሆነ እና በክርክር ሂደት በተጠሪ ተጠይቆ የመጣ በተጨማሪ ማስረጃነት የሚታይ እንጅ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 6 ድንጋጌ የሚጠይቀዉን መስፈርት የሚያሟላ እና አስቀድሞ የተሰጠዉ ፍርድ ሀሰተኛ ሰነድን መሰረት ተደርጎ የተወሰነ መሆኑን የሚያሳይ አይደለም ፡፡ ተጠሪ የጠቀሱት በሰበር መ/ቁ **42871 የተሰጠ** የሰበር ዉሳኔም ለዚህ ጉዳይ ተፈጻሚነት ያለዉ አይደለም ፡፡ በመሆኑም የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛዉ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 14302 በ13/07/2013 ዓ/ም በሁለተኛ ዳግም ዳኝነት አይቶ አስቀድሞ በ02/06/2007 የሰጠዉን ዉሳኔ መቀየሩ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 6 ድንጋጌ መስፈርት ያላገናዘበ እና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ተብሎ ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ዉሳኔ

በደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 14302 እና በመ/ቁ 22065 አንድ ላይ አጣምሮ መጋቢት 13 ቀን 2013 ዓ/ም የተሰጠዉ ዉሳኔ እና በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 0332283 የካቲት 08 ቀን 2015 ዓ/ም በአብላጫ ድምጽ የጸናዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ተብሎ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሸሯል፡፡

የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛዉ ፍርድ ቤት በመ/ቀ 14302 የካቲት 28 ቀን 2006 ዓ/ም እና የካቲት 02 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢ ነዉ ተብሎ ጸንቷል፡፡

በዚህ ችሎት ተሰጥቶ የነበረዉ የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል ለሚመለከተዉ ክፍል ይጻፍ፡፡

የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ም

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁጥር 243628

ጥቅምት 05ቀን 2017ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ብርሃኑ መንግስቱ

ማርታ ተካ

አመልካች፡- አቶ ሀይሌ ማንያዘዋል

ተጠሪ፡- አቶ አሬሮ ብሩ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩ ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች መጋቢት 04 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ በማጽናት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ በመሻር በመ/ቁ 406787 በቀን 11/04/2015 ዓ.ም መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በሚል ስላመለከቱ ነው፡፡

ጉዳዩ ይዞታን በማስለቀቅ ለመረከብ የቀረበ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በኦሮሚያ ክልል በያቤሎ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች ከሳሽ በመሆን የአሁን ተጠሪ 2ኛ ተከሳሽ፤ የዚህ ሰበር ክርክር ተካፋይ ያልሆነ የያቤሎ ከተማ መሬት ጽ/ቤት ስር 1ኛ ተከሳሽ ሆነው ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ሲታይ አመልካች ለወረዳ ፍርድ ቤት የቀረቡት አቤቱታ ይዞታው በያቤሎ ከተማ ገርቢ ያቤሎ ቀበሌ ልዩ ቦታው ኬላ ለየሚባል ቦታ ውስጥ የሚገኝ ስፋቱ 1000 ካ/ሜትር የሆነ የኢንቨስትመንት የተሰጠኝ እና ቀድሞ የአቶ ቴንደኬ ዋሪዮ የነበረ ቤት ያረፈበት በህግ አግባብ አስፈላጊውን

ካሳ በሙሉ ከፍዬ ስር 1ኛ ተከሳሽ የሆነው የያቤሎ ከተማ የመሬት ፅ/ቤት የመሬት ዕጣ ቁጥር A፣H2B2 በሆነ ስጥቶኝ ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2013 ዓ.ም የመንግስት ግብር ከፍዬ ህጋዊ ከአደረገልኝ በኋላ የከተማው ኮንስትራክሽ ፅ/ቤት ደግሞ በቀን 21/07/2013 ዓ.ም የግንባታ ፈቃድ የሰጠኝ ቢሆንም 1ኛ ተከሳሽ መብት ሳይኖረው በህጋዊ መልኩ ያገኘሁትን የመሬት ይዞታ በህገ ወጥ መንገድ 2ኛ ተከሳሽ ለሆነው የአሁኑ ተጠሪ ይዞታዬን አሳልፎ ከሰጠው በኃላ የአሁኑ ተጠሪ (ስር 2ኛ ተከሳሽ) በይዞታው ላይ ድንጋይ በቦታው ላይ የነበረው የአፈር ቤት ማንነቱ በማይታወቅ ግልሰብ እንዲቃጠል ያደረገ በመሆኑ ስር 1ኛ ተከሳሽ ጽ/ቤት ይዞታዬ ላይ ለተጠሪ የሰጠውን የባለይዞታነት ማረጋገጫ ወረቀት እንዲሰርዝ እና ተጠሪ ደግሞ ይዞታዬ ላይ የደፋውን ድንጋይ በራሱ ወጪ በማንሳት ይዞታዬ ለቆ ያስረክበኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ስር 1ኛ ተከሳሽ የሆነው የያቤሎ ከተማ መሬት ጽ/ቤት በሰጠው መልስ፡- ከመነሻው ክርክር ባስነሳው ይዞታ ላይ ቴንደኬ ዋሪዮ መብት የሌለው መሆኑን ይህ ይዞታ ከዚህ ቀደም የአቶ ኤሉ ያያ እንጅ የቴንደኬ ዋሪዮ አለመሆኑን፤ ካሳ የሚከፍለው መንግስት እንጂ አመልካች ለቴንደኩ ዋሪዩ ካሳ ከፍለው የይዞታው ባለቤት ሊሆኑ ስለማይችሉ ክሳቸው ውድቅ ሊሆን ይገባል የሚል ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪ(ስር 2ኛ ተከሳሽ) በበኩሉ ክርክር የተነሳበት ይዞታ እንደ ድርጅት መሬት እንዲሰጠኝስር 1ኛ ተከሳሽ ለሆነው ለያቤሎ ከተማ አስተዳደር መሬት ይዞታ ፅ/ቤትን ጥያቄ አቅርቤ ለድርጅት የሚሆን መሬት አሁን ለክርክር ምክንያት  የሆነውን 2000 ካ/ሜ የሆነ መሬት በህጋዊ መንገድ ተሰጥቶኝ የባለይዞታነት ማረጋገጫ (ሳይት ፕላን) በቀን 15/03/2013 በስሜ ተመዝግቦ የመንግስት ግብርም ከፍዬ እያስተዳደርኩ የምገኘው ይዞታ ሲሆን አመልካች ይህ መሬት ከአቶ ቴንደኬ ዋሪዮ ወደ እኔ ተላልፏል በማለት በምን አይነት ሁኔታ እንደተላለፈ የሚገልፅ ውል በሌለበት፤ ካለም ዉሉ በሚመለከተው አካል ቀርቦ ያልተረጋገጠ ስለሆነ ውድቅ መሆን አለበት፡፡ አቶ ቴንደኬ ዋሪዮ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው የመሬት ይዞታ 1000 ካ/ሜትር በህገወጥ መንገድ ይዞ ከብቶች በረት ገንብቶበት ስለነበረ ለከተማ ልማት ስራ ለማዋል ይህንን መሬት አቶ እንዲለቅ ድብዳቤ ሲፃፍላቸው የነበረ ሲሆን ይህን በመተላለፍ አቶ ቴንዴከ በይዞታው ላይ መብት ሳይኖረው ለሌላ ግለሰብ አሳልፎ መስጠቱ በህገ ተቀባይነት የለውም፡፡ ለአመልካች የይዞታ መረጋገጫ የተሰጠው በቀን 25/06/2013 ሲሆን ለእኔ ደግሞ አስቀድሞ በ15/03/2013 ዓ.ም የተሰጠ እና ዕጣ ቁጥር A1B በሆነ 1000 ካ/ሜትር ቦታ እና AE1B1  በሆነ 1000 ካ/ሜ በዚህ ይዞታ ላይ ተሰጥቶኝ በዚህም ረገድ የቅድሚያ መብት ያለኝ መሆኑን በሌላ በኩል ደግሞ የሳይት ፕላን ማስረጃ የተሰጠው በስህተት የተሰጠው እና ስር 1ኛ ተከሳሽን በማታለል የወሰደ ስለሆነ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡

የያቤሎ ወረዳ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን የሰው እና የሰነድ ማስረጃ ከመረመረ በኋላ በመ/ቁ 16980 በቀን 19/07/2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት አቶ ቴንደኬ ዋሪዮ አከራካሪው መሬት ላይ አንዳችም መብት ሳይኖረው ለአመልካች ያስተላለፈ መሆኑን፣ በያቤሎ ከተማ ገርቢ ያቤሎ ቀበሌ ዶሎሎ ሆላ የሚባል አካባቢ

የሚገኘውን ይዞታ ስፋቱ 2000 ካ/ሜትር የሆነ ስር 2ኛ ተከሳሽ የነበረ (የአሁኑ ተጠሪ) በመሆኑ አመልካች ምንም በአከራካሪው መሬት ላይ መብት የላቸውም በማለት ክሳቸውን ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካችም በውሳኔው ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለቦረና ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም በመ/ቁ 16682 ላይ በቀን 02/10/2014 ዓ.ም አመልካች አከራካሪው ይዞታ ለቴንደኬ ዋሪዩ ለተባለ ካሳ ከከፈለ በኃላ ህጋዊ በሆነ መልኩ የባለይዞታነት ማረጋገጫ ካርታ የተሰጠው መሆኑ በተረጋገጠበትና የአሁን ተጠሪ ክርክር ያስነሳው መሬት 1000ካ.ሜ ከተሰተው በኃላ ይህንኑ ክርክር ያስነሳው 1000ካ.ሜ ይዞታ የተጨመረለት መሆኑ ስለሚያሳይ ለአሁኑ ተጠሪ ተጨምሮ የተሰጠው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ አመልካች ካቀረበው ማስረጃ በበለጠ የሚያረጋግጥለት ሆኖ ስላልተገኘ የስር ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመሻር ክርክር ያስነሳው 1000 ካ/ሜትር ይዞታ የአመልካች ነው በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱም በመ/ቁ 407223 በቀን 02/02/2015 ዓ.ም ይግባኙን በመሰረዝ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

በመቀጠል የአሁን ተጠሪ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጿል በማለት አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤት በመ/ቁ 406787 በቀን 11/04/2015 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው የመሬት ይዞታ ላይ የባለ ይዞታነት ማረጋገጫ ወረቀት አስቀድሞ ለአሁን ተጠሪ በቀን 15/03/2013 ዓ..ም የተሰጠ በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ አንቀፅ 1196 እና 1197(1) መሰረት ለተጠሪ የሰተጠቅ የይዘታ ማረጋገጫ ካርታ ሳይሰረዝ፤የአሁን አመልካች በቀን 25/06/2013 ዓ.ም በተሰጠው የባለይዞታነት ማረጋገጫ ወረቀት ባለመብት የሚሆንበት ሁኔታ የሌለ በመሆኑ የአሁን ተጠሪ ለክርክር ምክንያት የሆነውን መሬት እንዲለቅ እና የተሰጠው የባለይዞታነት ማረጋገጫ ወረቀት እንዲሰረዝ የመወሰን ስልጣን ሳይኖረው ለተጠሪ የተሰጠው የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በሰጠው አካል በኩል እንዲሰረዝ እና ተጠሪ መሬቱን ለቀው ለአመልካች እንዲያስረክቡ በማለት የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ እና ይህንን ውሳኔም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ማጽናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ይግባኝ ሰሚ ችሎቶቹ የሰጡት ውሳኔም ሆነ ትእዛዝ በመሻር የወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔን በማፅናት ወስኗል፡፡

አመልካች በቀን 04/07/2015ዓ.ም ጽፈው ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡት አቤቱታ ይዘቱም ሲታይ፦ ለአመልካች ሆነ መልስ ሰጭ የባለይዞታነት ማረጋገጫ ወረቀት (ካርታ) ያለአግባብ ተሰርቶ ከሆነ የአስተዳደር ስነ-ስርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀፅ 52 መሰረት አስተዳደራዊ መፍትሔዎች ተሟጠው ማለቅ አለበት እንጅ ፍ/ቤት ጉዳዩ መታየቱ ስህተት መሆኑን በሌላ መልኩ አመልካች ቦታው ላይ 2006 ዓ.ም ጀምሮ ግብር ሲገብርበት እንደቆየሁ በህጋዊ ደረሰኝ ተረጋግጦ እያለ የያቤሎ ከተማ ማዘጋጃ ቤት በ2008 ዓ.ም ነው የተቋቋመው በማለት የአመልካችን ህጋዊ ደረሰኞች ውድቅ ለማድረግ የሄደበት አግባብ መሰረታዊ የማስረጃ ምዘና የተፈፀመበት ነው፡፡ከዚህ በተጨማሪም አመልካች ቦታውን ከ7 እስከ 8 ዓመት ድረስ በእጅ

አድርገው እየተጠቀመበት የቆዩ መሆኑ፣ አመልካች ላይ ያወጣው የይዞታ ማረጋገጫ ወረቀት አለመሰረዝ ሲታይ በፍ/ብ ህግ ቁጥር 1195፣ 1196 እና 1197 መሰረት ቦታውን በህጋዊነት ይዞ የሚገኘውን መልስ ሰጭ ሳይሆን አመልካች መሆኑን መረዳት እየተቻለ ቦታው ለመልስ ሰጭ ይገባል በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፡፡ አመልካች ለአቶ ተንተኬ ዋሪዮ ለተባሉ ግለሰብ ካሳ የከፈለው ከተማውን በሚያስተዳድር የአስተዳደር አካል እውቅና መሆኑን በማስረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ሆኖ እያለ  የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ይዞታው የመልስ ሰጭ ነው በማለት አግባብ የወሰነ በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም መዝገቡን በመመርመር ፍርድ ቤት የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ በሰጠው አካል በኩል እንዲሰረዝ የመወሰን ሥልጣን የለውም የመባሉ አግባብነት፣ እንዲሁም የይዞታ ማረጋገጫ መደራረብ(over lap) በይዞታው ላይ መብት አለን በሚሉ ተከራካሪዎች ላይ የሚያስከትለውን ሕጋዊ ውጤት ከህግ መንግስት አንቀፅ 37፤ በሰበር መዝገብ ቁጥር 75414 እና 9907፤ በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1553-1636 አንፃር በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 ቁጥር 2/4) (ሀ)፤ (ሽ)እና ቁጥር 10(ሐ)፤ አንቀፅ 28(3) እንዲሁም በመመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 7/3 መሰረት በመድረግ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ታዟል፡፡

ተጠሪም በቀን 07/02/2016 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ በመልሳቸውም በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ የተሰጠው ጥቅምት 02 ቀን 2015 ዓ.ም ሲሆን የሰበር አቤቱታ የቀረበው ግን መጋቢት 04 ቀን 2015 ነው፡፡ በመሆኑ ይህ ከ90 ቀናት በላይ ስለሆነ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 27/3 መሰረት የአመልካች አቤቱታ በይርጋ የታገደ ነው፡፡

እንዲሁም በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ሆነ በዚህ ችሎት የጠየቁት ዳኝነት በህግ ውጭ ተሰጥቷል የሚሉት የተጠሪ ካርታ ይሠረዝልን የሚል መሆኑን ግልፅ ነው፡፡ፍርድ ቤቶች የመሬት ይዞታ መብት ምዝገባ (ካርታ) ሕጋዊነትን ወይም ካርታው ሊሠረዝ ይገባል በማለት የሚነሱ ጉዳዮችን በተመለከተ አግባብነት ያለውን የህግ ሥርዓትና ደንቡን ተከትሎ የተፈፀመ መሆን አለመሆኑን በማስረጃ አጣርተው የመወሰን ሥልጣን ያለቸው መሆንን የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 9907፣91612፣75414፣ 67011፣ እና በሌሎች መዝገቦች አስገደጅ ውሳኔ የህግ ትርጉም ተሰቷል፡፡አመልካች የግብር ደረሰኝ መታየት ነበረበት በማለት በማስረጃ አቀባበልና ምዘና ላይ ተመስርተው ያነሱት ክርክር የህግ መሰረት የሌለው ነው፡፡ በግለሰቦች መካከል አንዱ ለሌላው በቀጥታ የካሣ ክፍያ የሚፈፀምበት ሆነ በዚህ አሰራር ይዞታ የሚተላለፍበት ህጋዊ አግባብ የለም፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሊዝ አዋጅ 721/2004 መሰረት የአመልካች ለግለሰብ ካሳ ከፍያለው በማለት ያነሱትን መንቀፍ አግባብ ነው፡፡ ካርታው የሰጠው አካል በኩል መሰረዝ አለበት የለበትም የሚለው በስር ፍ/ቤት ሆነ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት አልተነሳም፡፡ አስቀድሞ የተጠሪ መብት ከተፈጠረበት ከ2000 ካ/ሜትር ይዞታ ላይ ግማሽ ተቆርሶ ለአመልካች ተሰጠ የሚባል እንጅ ሁለት ተጎራባች የሆነ ይዞታዎች እንደሆኑና የአንዳኛው የመሬት ይዞታ ክፍል የተወሰነ አካል በሌላው ተጎራባች

ይዞታ እንደረፈ ተደርጎ ሊቆጠር አይገባም፡፡በመሆኑም የአመልካች አቤቱታ ውድቅ መሆን አለበት በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም እንደሚከተለው መርምሯል፡፡ በዚህ ሰበር መዝገብ ተጣርቶ እልባት ማግኘት ያለባቸው ነጥቦች፡-

1. የአመልካች ሰበር አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜ ካለፈው በኃላ የቀረበ ነው ወይስ አደለም?
2. የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የስር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶቹ የሰጡት ውሳኔ በመሻር የወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ በማጽናት ሲወስን ፍርድ ቤት የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲሰረዝ የመወሰን ስልጣን ማለቱ ተገቢ ነው ወይስ አደለም? እንደአጠቃላይ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑ ጭምር እንዲሚከተለው መርምረናል፡፡

<u>የመጀመሪያው ጭብጥ ስንመለከት፡-</u> እንደሚታወቀው የሰበር ጥያቄ ማመልከቻ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መቅረብ የሚገባው የሰበር ጥያቄ በሚቀርብበት ጉዳይ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ከተሰጠ ጀምሮ ባሉት 90(ዘጠና) ቀናት ውስጥ መሆኑን በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ27(3) ስር ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ተጠሪ ለሰበር አቤቱታው በሰጡት መልሳቸው የአመልካች ሰበር አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜው ካለፈ በኃላ የቀረበ በመሆኑ በይርጋ ሊታገድ ይገባል በሚል የተቃወሙ ሲሆን ይህ ሰበር ችሎትም አመልካች ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜ ካለፈ በኃላ ነው ወይስ አደለም የሚለው ነጥብ ስንመለከት አመልካች ሰበር አቤቱታ ለማቅረብ ምክንያት የሆናቸው ውሳኔ በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቀን 11/04/2015 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ ሲሆን ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት በቀን 04/07/2015 ዓ.ም ነው፡፡ ይህም ማለት በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የመጨረሻ ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ባቀረበበት መካከል ያለው ጊዜ ሲቆጠር 90 ቀናት ሳይሞላው ሰበር አቤቱታው መቅረቡ የሚያሳይ በመሆኑ በተጠሪ በኩል የአመልካች ሰበር አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜ በይርጋ የታገደ ነው በሚል ያቀረቡት መከራከሪያ ነጥብ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

<u>ሁለተኛው ጭብጥ ስንመለከት</u>፡- የአሁኑ አመልካች በክሳቸው የሚጠይቁት ዳኝነት ስር 1ኛ ተከሳሽ በህጋዊ መንገድ ያገኙሁት ይዞታ በህገወጥ መንገድ ለአሁኑ ተጠሪ በመስጠት በዚሁ ይዞታዬ ላይ በተጠሪ ስም የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የሰጠ በመሆኑና ተጠሪም አላግባብ ይዞታዬ የያዘ በመሆኑ ስር 1ኛ ተከሳሽ ለተጠሪ የሰጠው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንዲሰርዝ፤ ተጠሪም ይዞታዬ ለቆ ሊያስረክበኝ ይገባል የሚል ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ክርክሩ በግራ ቀኙ ማስረጃ እንዲጣራ ከተደረገ በኃላ በሚደረስበት ውጤት መሰረት ተገቢው ውሳኔ የሚሰጥበት ከሚሆን በቀር የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

በፍርድ ቤት ሊስተናገድ የሚችል አይደለም ከሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡ ከማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ሕጋዊነት እና ተቀባይነት ጋር ተያይዞ የምስክር ወረቀቱ ሊሰጥ የቻለው ባለሀብትነት ሊተላለፍ ስለሚችልበት አግባብ  በሕጉ የተመለከተውን ሕግና ስርዓት ሳይከተል በመሆኑ ንብረቱ የተላለፈለት ሰው የንብረቱ ባለሀብት ስለመሆኑ ግምት የሚያስወስደው የባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ቀሪ ነው፣ሊሰረዝ ወይም ሊስተካከል ይገባል በሚል የሚቀርብ ክስ በፍርድ ቤት ሊስተናገድ እና ዳኝነት ሊሰጥበት የሚችል ስለመሆኑ ይህ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 75414 በ22/02/2005 ዓ.ም. እና በሌሎችም መዝገቦች አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥተዋል፡፡ በመሆኑም በክርክሩ ከሚረጋገጡት ፍሬ ነገሮች አንጻር በአስተዳደር አካሉ ለተጠሪ የተከናወነው የስም ዝውውር ሊቃና ይገባል ወይስ አይገባም? በሌላ አነጋገር አለአግባብ የተሰጠ ነው የተባለው የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ ሊሰረዝ ይገባል ወይስ አይገባም? በሚለው የክርክር ጭብጥ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ እንደ የክርክሩ ባሕርይ እና ይዘት የሚወሰን መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ፍርድ ቤት የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በሰጠው አካል በኩል እንዲሰረዝ የመወሰን ስልጣን የለውም በሚል በፍርድ ሀተታው ላይ ማስፈሩ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ሌላው አመልካች ያነሱት ግብር በ2006 ዓ.ም ጀምሮ እያገበርኩ እንደ ነበር በህጋዊ ደረሰኞች ተረጋገጦ እያለ የያቤሎ ከተማ የተቋቋመው 2008 ዓ.ም ነው በማለት ደረሰኞቹን ውቅድ ማድረጉ አግባብ አይደለም፤ በቦታው ከ7 ዓመት እስከ 8 ዓመት ድረስ በእጅ አድርጌ እያተጠቀምኩ ነው፤ እንዲሁም ካሳ የከፈልኩ በከተማው አስተዳደር እውቅናነው፣ ለዚህም ከተማው እውቅና በመስጠት የይዞታ መረጋገጫ ሰጥቶኛል በማለት ያነሱ ሲሆን ይህ በተመለከተ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በአዋጅ ቁጥር 721/2004 እና በፍ/ብ/ህግ 1195 እና ተከታይ ድንጋጌዎች እንዲሁም አዋጅ ቁጥር 1161/2012 መሰረት በማድረግ የግራ ቀኙ ክርክር መርምሮ ተጠሪ ከአመልካች አስቀድሞ አከራካሪው ይዞታ ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የተሰጠው በመሆኑ ይህ የተሰጠው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ከህግ አግባብ ውጪ የተሰጠው ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ በአከራካሪው ይዞታ ላይ ቀደምት መብት ያለው ተጠሪ በመሆኑ ክርክር ያስነሳው ይዞታ ለቆ ለአሁኑ አመልካች ሊያስረክብ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 40/3 መሰረት የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግስትና የሕዝብ ብቻ ነው፡፡ መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች ሕዝቦች የጋራ ንብረት ነው በማለት ይደነግጋል፡፡ እንዲሁም አዋጅ ቁጥር 721/2004 መሰረት መሬት ሊተላለፍ የሚችለው በመንግስት አካል መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ የአሁኑ አመልካች ክርክር ያስነሳው ይዞታ ሲጠቀም ለነበረ ለግለሰብ ካሳ ከፍለው ከያዙት በኃላ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የተሰጣቸው መሆኑን ገልጸው የሚከራከሩ ሲሆን ካሳ የሚከፍለው መንግስት እንጅ ግለሰብ ለመሬት ካሳ በመክፈል የይዞታው ባለቤት ሊሆን የሚችልበት የህግ አግባብ

**ማስታወሻ፡** - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ባለመኖሩ እንዲሁም አመልካች ካሳ ከፈልኩ የሚሉት ግለሰብም በይዞታው ላይ መብት ያልነበረው መሆኑ በስር ወረዳ ፍርድ ቤት ተረጋግጧል እንዲሁም ከከተማ ይዞታ ጋር በተያያዘ በተጠሪም ሆነ ለአመልካች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በመሰጠቱ የይዞታ ማረጋገጫ መደራረብ (overlap) ሲያጋጥም በይዞታው ላይ መብት አለን በሚሉ እነዚህ ተከራካሪዎች ላይ የሚስከትለው ሕጋዊ ውጤት በተመለከተ ሁለት እና ከዛ በላይ የሆኑ ግለሰቦች በተመሳሳይ ይዞታ ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ካላቸው መጀመሪያ የይዞታ ማረጋገጫ የተሰጠው ሰው ህጋዊ ባለይዞታ እንደሆነ ስለ ከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 818/2006 አንቀፅ 43(1) በግልፅ ተደንግጓል፡፡ በዚህ ጉዳይም በአከራካሪው ይዞታ ላይ ቅድሞያ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የተሰጠው ለአሁኑ ተጠሪ መሆኑና ይህ የተሰጠው ይዞታ ማረጋገጫ ካርታም በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1195 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሰረት ለተጠሪ የተሰጠው የባለቤትነት ግምት ሊያስተባብል በሚችል መልኩ ካርታው የተሰጠው ከህግ አግባብ ውጪ ስለመሆኑ የአሁኑ አመልካች ባላስረዱበት ሁኔታ ተጠሪ አከራካሪውን ይዞታ ለቆ ለአመልካች እንዲያስረክብ የሚወሰንበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጠሪ አከራካሪው ይዞታ ለቆ ለአመልካች ሊያስረክብ አይገባም በማለት የስር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶች ውሳኔ በመሻር የወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ በማጽናት መወሰኑ በውጤት ደረጃ በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4) እና 10/1(ሐ)እና(መ) ስር ከተዘረዘሩት መመዘኛዎች አንጻር በማየት መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት አላገኘንበትም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1. የያቤሎ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 16980 በቀን 19/07/2014 የሰጠው ውሳኔ እና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት በመ/ቁ 406787 በቀን 11/04/2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በውጤት ደረጃ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9/1 መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ወጪና ክሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ም

ት የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግስትና የሕዝብ ብቻ ነው፡፡ መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች ሕዝቦች የጋራ ንብረት ነው በማለት ይደነግጋል፡፡ እንዲሁም አዋጅ ቁጥር 721/2004 መሰረት መሬት ሊተላለፍ የሚችለው

በመንግስት አካል መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ የአሁኑ አመልካች ክርክር ያስነሳው ይዞታ ሲጠቀም ለነበረ ለግለሰብ ካሳ ከፍለው ከያዙት በኃላ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የተሰጣቸው መሆኑን ገልጸው የሚከራከሩ ሲሆን ካሳ የሚከፍለው መንግስት እንጅ ግለሰብ ለመሬት ካሳ በመክፈል የይዞታው ባለቤት ሊሆን የሚችልበት የህግ አግባብ ባለመኖሩ እንዲሁም አመልካች ካሳ ከፈልኩ የሚሉት ግለሰብም በይዞታው ላይ መብት ያልነበረው መሆኑ በስር ወረዳ ፍርድ ቤት ተረጋግጧል እንዲሁም ከከተማ ይዞታ ጋር በተያያዘ በተጠሪም ሆነ ለአመልካች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በመሰጠቱ የይዞታ ማረጋገጫ መደራረብ (overlap) ሲያጋጥም በይዞታው ላይ መብት አለን በሚሉ እነዚህ ተከራካሪዎች ላይ የሚስከትለው ሕጋዊ ውጤት በተመለከተ ሁለት እና ከዛ በላይ የሆኑ ግለሰቦች በተመሳሳይ ይዞታ ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ካላቸው መጀመሪያ የይዞታ ማረጋገጫ የተሰጠው ሰው ህጋዊ ባለይዞታ እንደሆነ ስለ ከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 818/2006 አንቀፅ 43(1) በግልፅ ተደንግጓል፡፡ በዚህ ጉዳይም በአከራካሪው ይዞታ ላይ ቅድሞያ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የተሰጠው ለአሁኑ ተጠሪ መሆኑና ይህ የተሰጠው ይዞታ ማረጋገጫ ካርታም በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1195 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሰረት ለተጠሪ የተሰጠው የባለቤትነት ግምት ሊያስተባብል በሚችል መልኩ ካርታው የተሰጠው ከህግ አግባብ ውጪ ስለመሆኑ የአሁኑ አመልካች ባላስረዱበት ሁኔታ ተጠሪ አከራካሪውን ይዞታ ለቆ ለአመልካች እንዲያስረክብ የሚወሰንበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጠሪ አከራካሪው ይዞታ ለቆ ለአመልካች ሊያስረክብ አይገባም በማለት የስር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶች ውሳኔ በመሻር የወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ በማጽናት መወሰኑ በውጤት ደረጃ በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4) እና 10/1(ሐ)እና(መ) ስር ከተዘረዘሩት መመዘኛዎች አንጻር በማየት መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት አላገኘበትም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

1. የያቤሎ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 16980 በቀን 19/07/2014 የሰጠው ውሳኔ እና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት በመ/ቁ 406787 በቀን 11/04/2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በውጤት ደረጃ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9/1 መሰረት ፀንቷል፡፡

2. ወጪና ክሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ም

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መዝገብ ቁጥር 243809

ጥቅምት 07 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች፡- ወ/ሮ ለምለም ጌታቸው - ጠበቃ አቶ መሠረት አባዬ ቀርቧል

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. ወ/ሮ እርስቴ ዓለሙ

2ኛ. ወ/ሮ ሰላማዊት ዓለሙ — አልቀረቡም

3ኛ. አቶ ነጋሽ ዓለሙ

4ኛ. ወ/ሮ አልማዝ ዓለሙ

5ኛ. ወ/ሮ ገነት ዓለሙ

6ኛ.ወ/ሮ ደመቀች ዓለሙ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የውርስ ማጣራትን የሚመለከት ሆኖ ተጠሪዎች ግንቦት 24 ቀን 2013 ዓ.ም አሻሽለው ለፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረቡት አቤቱታ የሟች ወላጆቻቸውንና የአያታቸውን ወራሽነት እንዳረጋገጡ ገልፀው የአባታቸው አቶ ዓለሙ ጌታቸው፤ የእናታቸው ወ/ሮ ድንበርሸወርቅ እሸቴ፤

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

እንዲሁም የአያታቸው አቶ ጌታቸው ሀብተማሪያም ውርስ የሚያጣራ የውርስ አጣሪ እንዲሾምላቸው ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት አግኝቶ ውርሱ እንዲጣራ ትዕዛዝ ከተሰጠ በኋላ አመልካች እና በሰበር ክርክሩ የሌሉት ወ/ሮ መሠረት ዓለሙ እና ወ/ሮ አሰለፈች ዓለሙ ጣልቃ እንዲገቡ ተፈቅዶላቸው ውርሱም ተጣርቶ ቀርቦ ግራ ቀኙ በውርስ አጣሪ ሪፖርቱ ላይ ያላቸውን አስተያየት አቅርበዋል፡፡ አቤቱታው የቀረበለት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም የቤት ቁጥር 1189 የሟች አቶ ጌታቸው ሀብተማሪያም መሆኑ አከራካሪ አለመሆኑንና አከራካሪ የሆነው ጉዳይ የቤት ቁጥር 1188 መሆኑን ጠቅሶ የዚህ ቤት ግብር በሟች አቶ ጌታቸው ስም ሲከፈል እንደቆየ የቀረቡት ማስረጃዎች የሚያስረዱ ቢሆንም በሟች አቶ ዓለሙ ጌታቸው የተሰሩት 10(አሥር) ክፍል ቤቶች የሟቹ ሲሆኑ ቀሪው የሟች አቶ ጌታቸው ሀብተማሪያም የውርስ ሀብት ሊሆን እንደሚገባ ገልጸ አመልካች የሟች ወ/ሮ አስቴር ልጅ መሆናቸው መረጋገጡን ገልጸ የግራ ቀኙ ድርሻ በሪፖርቱ ላይ በተመለከተው አግባብ ነው በማለት የፍትሐ ብሔር ሕጉን ቁጥር 1179/1 ጠቅሶ ወስኗል፡፡ አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ያቀረቡት የይግባኝ አቤቱታ ይግባኝ ሰሚው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 337 መሠረት በመሠረዙ የሰበር አቤቱታ ለዚህ ችሎት አቅርበዋል፡፡

አመልካች ያቀረቡት የሰበር ቅሬታ ይዘት በአጭሩ፡- ተጠሪዎች ውርስ አጣሪው ዘንድ ያቀረቡት ክርክር ሟች አቶ ጌታቸው ሀብተማሪያም ከነበራቸው 500 ካ.ሜ ይዞታ ላይ 250 ካሬ ሜትሩን ታህሳስ 16 ቀን 1981 ዓ.ም በተፃፈ የስጦታ ውል ለሟች አቶ ጌታቸው ዓለሙ ሰጥተው ሟቹም ይህንን ይዞታ ከነባር ይዞታቸው ጋር አጠቃለው አልምተው ሲጠቀሙ ቆይተው በስማቸው መመዝገቡን እንጅ በባዶ መሬት ላይ ያለምንም ተቃውሞ 10(አስር) ክፍል ቤቶችን መሥራታቸውን ጠቅሰው በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1179 መሠረት የቤቱ ባለቤት አቶ ዓለሙ ጌታቸው ናቸው በማለት ያቀረቡት ክርክር በሌለበት የውርስ አጣሪ ሪፖርቱ ለፍርድ ቤት ከቀረበ በኋላ ያቀረቡት አዲስ ክርክር በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 329/1 መሠረት ተቀባይነት የሌለው ሆኖእያለ ዳኝነት ያልተጠየቀበትንና በጭብጥነት ተይዞ ክርክር ያልተደረገበትን የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1179 ተጠቅሶ የቤት ቁጥር 1188 ከፊሉ የሟች አቶ ዓለሙ ጌታቸው የውርስ ሀብት ነው የሚለው የፍርዱ ክፍል የሕግ መሠረት የለውም፡፡ ክርክሩ አለመቅረቡ እንደተጠበቀ ሆኖ የቤት ቁጥር 1188 እና 1189 በአንድ ግቢ ውስጥ በ501 ካ.ሜ ይዞታ ላይ የሚገኝ ዋና ቤት እና 13 ክፍል የሚከራዩ ቤቶች እንደሆኑ ምስክሮች ያስረዱ ሲሆን ፤ ቤቶቹ ያረፉበት ይዞታ የሟች አቶ ጌታቸው ሀብተማሪያም መሆኑ በደብዳቤ መገለጹን ፤ የቤት ቁጥር 1189 በሟች አቶ ጌታቸው ስም ተሰርቶ የነበረው ካርታ የቤት ቁጥር1188ን አካቶ ካርታ ተሰርቶ መጽደቁ ፤ የቤት ቁጥር 1188/1189 የአቶ ጌታቸው ሀብተማሪያም ንብረት ነው ተብሎ በቅጽ 008 መመዝገቡን የሚያመለክት የሰነድ ማስረጃ የቀረበ ሲሆን ከ1968 ዓ.ም እስከ 2014 ዓ.ም ድረስ በሟች አቶ ጌታቸው ሀብተማሪያም ስም ግብር ሲከፈል የነበረ መሆኑ፣ የቤት ቁጥር 1188 እና 1189 የሟች አቶ ጌታቸው ሀብተማሪያ የግል ንብረት መሆኑን ሟች አቶ ዓለሙ ጌታቸውም አምነው

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በወራሽነታቸው ካርታ እንዲሰራላቸው ለጉለሌ ክፍል ከተማ መሬት አስተዳደር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን በአጠቃላይ የቤት ቁጥር 1188 እና 1189 ወይም የቤት ቁጥር 1188/1189 ግብር የሚከፈልበት 501 ካ.ሜ እና ከግብር ውጪ የሆነው 779 ካ.ሜ ይዞታ ላይ ያረፈው ንብረት የአቶ ጌታቸው ሀብተማሪያም መሆኑ በሰው እና በሰነድ ማስረጃ ተረጋግጦ እያለ የሥር ፍርድ ቤት በማስረጃ ከተረጋገጠው ውጪ በአቶ ዓለሙ ጌታቸው የተሰሩት 10(አሥር) ክፍል ቤቶች የሚቹ የውርስ ሀብት ናቸው በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍል የማስረጃም ሆነ የሕግ መሠረት ስለሌለው ሊሰረዝ ይገባል፡፡ በአመልካች ወላጅ እናት በሟች ወ/ሮ አስቴር ጌታቸው የተሰሩትን 3 ክፍል ቤቶች እና አንድ መጋዘን ከሟች አቶ ጌታቸው ሀብተማሪያም እና ከሟች አቶ ዓለሙ ጌታቸው ውርስ ውጪ ሊሆን ሲገባ በዝምታ መታለፉ አግባብነት የለውም፡፡ የቤት ቁጥር 1189 ከቤት ቁጥር 1188 ጋር አንድ ግቢ ውስጥ በአንድ ላይ የሚገኝ እና የቤቶቹም ብዛት በተናጥል መግለጽ የማይቻል ፤ ግብር የሚገበርበት ይዞታስፋቱ 501 ካ.ሜ መሆኑ ፤ የቤት ቁጥር 1188 በአንድ ብሎክ እና ፓርሴል የሟች አቶ ጌታቸው ሀብተማሪያም የውርስ ንብረት መሆኑ ከታመነው የቤት ቁጥር 1189 ጋር ተቀላቅሎ ባለበት የሟች አቶ ዓለሙ ጌታቸው ናቸው የተባሉት 10 ክፍል ቤቶች የትኞቹ እንደሆኑ በግልጽ ተለይቶ ሊፈፀም የሚችል ፍርድ አለመሰጠቱ ተገቢ ስላልሆነ ስህተቱ ታርሞ ቁጥሩ 1188 የሆነው ቤት ከነሙሉ ይዞታው የሟች አቶ ጌታቸው ሀብተማሪያም የውርስ ንብረት ነው ተብሎ እንዲወሰን ጠይቋል፡፡

በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 6/1 መሠረት ለሰበር ሰሚው ችሎቱ የተመራው አቤቱታ በሰበር ሰሚ ችሎቱ ተመርምሮ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው የቤት ቁጥር 1188 ንብረትነቱ የአቶ ጌታቸው ሀብተማሪያም ሆኖ በዚሁ ቤት ይዞታ ላይ ያሉ 10 ክፍል ቤቶች በተጠሪዎች አባት ስለተሰሩ የአቶ ጌታቸው ሀብተማሪያም የውርስ ሀብት አይደሉም በሚል የመወሰኑን አግባብነት በውርስ ማጣራቱ ሂደት ከቀረበው ክርክር እና ማስረጃ ፤ ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር አንፃር ለመመርመር የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪዎች ተከታዩን መልስ ሰጥተዋል፡፡ ቁጥሩ 1188 የሆነው መኖሪያ ቤት የሟች አቶ ዓለሙ ጌታቸው መሆኑ ከመረጋገጡ ውጪ የሟች አቶ ጌታቸው ሀብተማሪያም የውርስ ሀብት ለመሆኑ ማስረጃ አልቀረበም፡፡ ቁጥሩ 1188 የሆነውን ቤት አቶ ዓለሙ ጌታቸው ከ1967 ዓ/ም በፊት 4(አራት) ክፍል ቤት ሰርቶ ከቆዩ በኋላ ወላጅ አባታቸው አቶ ጌታቸው ሀብተማሪም ታህሳስ 16 ቀን 1981 ዓ.ም ሕጋዊ ከሆነው 500 ካ.ሜ ይዞታቸው የሰጡትን 250 ካ.ሜ ይዞታ ክፍት (ባዶ) ከሆነው ይዞታ ጋር አጠቃሎ በማልማት ትዳር መስርቶ ተጠሪዎችን ወልዶ በሂደት ተጨማሪ ቤቶችን አስፋፍቶ የሰራ መሆኑና አሁን ላይ በተጠሪዎች እጅ መኖሩ በማስረጃ የተረጋገጠ ሲሆን ይህ ቤት ከመነሻው በሟች አቶ ዓለሙ ጌታቸው ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ሲሆን በቀድሞ አጠራር የወረዳ 8 ቀበሌ 35 ማሕበራዊ ፍርድ ቤት ይሕ ቤት የሟች አቶ ዓለሙ ጌታቸው መሆኑን ተረጋግጦ ለሥራና ከተማ ልማት እንዲፃፍላቸው ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ የሟች አቶ ጌታቸው ሀብተማሪያም የግል ንብረት የሆነው በ150 ካ.ሜ ይዞታ ላይ ያረፈው የቤት ቁጥር 1189

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የሖነው ሁለት ክፍል ቤት ሲሆን ሟች አቶ ዓለሙ ጌታቸው ከአበታቸው በስጦታ ያገኙትን ነባር ይዞታ እና በተጨማሪ የያዙትን ክፍት ቦታ በማካተት በቤት ቁጥር 1188 በስማቸው መብራት እና ውሃ አስገብተው የባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት በእቅስቃሴ ላይ እያሉ የሞቱ ሲሆን በቤት ቁጥር 1188 ላይ መጋዘኖችን የሰሩት ሟች ወ/ሮ ድንበርሸወርቅ እሸቴ ስለሆኑ አመልካች መብትና ጥቅም የሌላቸው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ የቤት ቁጥር 1188 እና 1189 እያንዳንዳቸው በምን ያህል ይዞታ ላይ እንዳረፉ እና በማን ቁጥጥር ስር እንደሆኑ ተጣርቶ ቀርቦ ውሳኔ እንዲያገኝ ተጠሪዎች ያቀረቡት አስተያየት በዝምታ መታለፉ አፈፃጸሙን አስቸጋሪ ቢያደርገውም በአጠቃላይ የቤት ቁጥር 1188 የሟች አቶ ዓለሙ ጌታቸው የውርስ ሀብት መሆኑ በወረዳው እና በምስክሮች ከመረጋገጡ ውጭ የሟች አቶ ጌታቸው ሀብተማሪያም የውርስ ሀብት ለመሆኑ ምንም ዓይነት ማስረጃ ስላልቀረበ የሰበር አቤቱታው ውድቅ ሊሆን ይግባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካችም የሰበር አቤቱታውቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለ መልኩ የተመለከተው የግራ ቀኝ ክርክር እና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ውሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንፃር የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለው ሕግ እና የሰበር ሰሚ ችሎቱ በጉዳዩ ላይ ከሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደሚታወቀው አንድ ፍርድ መፈጸም ያለበት በዋናው ክርክር በተሰጠው አግባብ መሆን እንደሚገባው የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 373 ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ አንድን ፍርድ በዋናው ክርክር ከተሰጠው ፍርድ ይዘትና ዓላማ ውጭ ማስፈጸም ይህን የህግ ድንጋጌ ይቃረናል፡፡ የሰበር ሰሚ ችሎቱም በሰበር መዝገብ ቁጥር 152172 (በቅጽ 23 እንደታተመው) የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 372 ፣378 እና ተከታዮቹን ድንጋጌዎችን መሰረት በማድረግ በሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ በሕግ አግባብ ታይቶ የተሰጠ ፍርድ እንደፍርዱ መፈጸም እንዳለበት አስገዳጅ ውሳኔ የሰጠ ሲሆን አንድ ፍርድ እንደፍርዱ ማስፈፀም እንዲቻል ፍርዱ ግልጽ መሆን እንዳለበት የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 183/1 ድንጋጌ ያመለክታል፡፡

በተየዘው ጉዳይ ተጠሪዎች ውርስ እንዲጣራላቸው የጠየቁት ንብረትነቱ የሟች አባታቸው አቶ ዓለሙ ጌታቸው ስም የተመዘገበ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 የሚገኝ የቤት ቁጥር 1188 ፣ እንዲሁም ሟች አባታቸው አቶ ዓለሙ ጌታቸውን በመተካት በሟች አያታቸው አቶ ጌታቸው ሀብተማሪያም ስም የተመዘገበ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 የሚገኝ የቤት ቁጥር 1189 እና ሌሎች የሰበር አቤቱታ ያልቀረበባቸው ንብረቶች በውርስ ሀብትነት ተጣርቶ የውርስ ድርሻቸው እንዲለይላቸው ጠይቀዋል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አመልካችም በተሸሻለው የጣልቃ ገብነት አቤቱታቸው ሟች እናታቸው ወ/ሮ አስቴር ጌታቸውን በመተካት የአያታቸው አቶ ጌታቸው ሀብተማሪያም ወራሽ መሆናቸውን በመግለጽ በሟች ስም የተመዘገቡ የቤት ቁጥር 1188 እና 1189፤ እሳቸውንና ሌሎች ጣልቃ ገቦችን ስለሚመለከት ድርሻችን ይለይልን በማለት ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪዎችም በጣልቃ ገብነት አቤቱታው ላይ በሰጡት መልስ የአመልካች እናት የሖኑት ወ/ሮ አስቴር የአቶ ዓለሙ ጌታቸው ልጅ እንጅ የአቶ ጌታቸው ሀብተማሪያም ልጅ ስላልሆነች እና ልጅ ለመሆኗም ማስረጃ ስላልቀረበ ከተጠሪዎች እኩል እንጅ የተለየ ድርሻ የሌላቸው መሆኑን፤ አቶ ጌታቸው ሀብተማሪም 250 ካ.ሜ መሬት ለአቶ ዓለሙ ጌታቸው ሰጥተው አቶ ዓለሙ ጌታቸው ከ1967 ዓ.ም በፊት የቤት ቁጥር 1188 አራት ክፍሎች መስራቱን ገልፀው ቤቱ የሟች አቶ ዓለሙ ጌታቸው ስለሆነ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾቹ ለሆኑት ለተጠሪዎች ልሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ በውርስ ማጣራቱ ሂደቱ ቤቶቹን ማን እንደሰራቸው ለማጣራት የግራ ቀኙ ምስክሮች የተሰሙ ሲሆን ጉዳዩ ከሚመለከተው የመንግስት አካል ማጣራት ተደርጓል፡፡ በዚሁ አግባብ የቤት ቁጥር 1189 የሟች አቶ ጌታቸው ሀብተማሪያም መሆኑ፤ የቤት ቁጥር 1188 አሥር ክፍሎች በሟች አቶ ዓለሙ ጌታቸው መሰራታቸው ፤ የቤት ቁጥር 1189 ከቤት ቁጥር 1188 ጋር በአንድ ገቢ ውስጥ የሚገኙ መሆኑን ፤ በግቢው ውስጥ ያለውን የቤት ብዛት በአንድ ላይ እንጅ ለብቻው (በተናጥል) መግለጽ የማይቻል መሆኑን ፤ ሁለቱም የቤት ቁጥሮች በብሎክ 28 ፤ ፓርሴል 13 ላይ የሚገኙ መሆኑን ፤ የቤት ቁጥር 1188 ያረፈበት ይዞታ ስፋት መግለጽ የማይቻል መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ቤቶቹ በአንድ ገቢ ውስጥ የሚገኙ ቢሆንም የቤት ቁጥር 1189 በሟች አቶ ጌታቸው ሀብተማሪያም ስም ካርታ ተሰርቶ የነበረ ሲሆን የቤት ቁጥር 1188 አሥር ክፍሎች በሟች አቶ ዓለሙ ጌታቸው የተሰሩ እና ከ1976 ዓ.ም ጀምሮ ማኅደር በስማቸው ተከፍቶ በስማቸው መመዝገቡን ከወሳኝ ኩነት ማስረጃ የቀረበ ከመሆኑ አንፃር ይዞታው የአንድ ሰው እንደሆነ ተወስዶ የቤት ቁጥር 1188 በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 1178 መሠረት የንብረት ባለሀብትነት መብት እንደተቋቋመበት መወሰዱ አግባብነት ባይኖረውም የቤት ቁጥር 1188 አሥር ክፍሎች በሟች አቶ ዓለሙ ጌታቸው የተሰሩ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጦ አሥሩ ክፍሎች የሟች አቶ ዓለሙ ጌታቸው ናቸው መባሉ አግባብ ቢሆንም በሟች አቶ ዓለሙ ጌታቸው የተሰሩት አሥሩ ክፍሎች በምን ያህል ካሬ ሜትር ላይ እንዳረፉ ፤ የቤቶቹ አቀማመጥ የሚያሳይ እስኬች በባለሞያ ተሰርቶ ቀርቦ መግቢያ መውጫው ተለይቶ ሊፈፀም የሚችል ውሳኔ አለመሰጠቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 83722 ጥቅምት 14 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ ፤ ውሳኔ እና ትዕዛዝ ፤ እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 299734 መጋቢት 1 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ- ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 9/1(ለ) መሠረት ተሻሽሏል።

2. በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 ውስጥ የሚገኝ የቤት ቁጥር 1188 አሥር ክፍል ቤቶች የሟች አቶ ዓለሙ ናቸው የሚለው እና የሰበር ቅሬታ ያልቀረበበት የውሳኔ ክፍል አልተነካም(ፀንቷል)፡፡
3. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በውሳኔ የዘጋውን የመዝገብ ቁጥር 83722 አንቀሳቅሶ በሟች አቶ ዓለሙ ጌታቸው የተሰሩት አሥር ክፍሎች ያረፉበት የይዞታ መጠን ፣ እንዲሁም መግቢያ መውጫው በባለሞያ እስኬች ተሰርቶ እና ተጣርቶ ሕጋዊ ውሳኔ እንዲሰጥ በሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 9/2 መሠረት መዝገቡ ተመልሶለታል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የሰ/መ/ቁጥር 243822

ቀን ፡- ጥቅምት 08 ቀን 2017 ዓ/ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካቾች፡- 1. አያል ደምሴ -
2. እታለም ደምሴ } አልቀረቡም

ተጠሪ ፡- ቢሳት ደምሴ - ወኪል ደሳለኝ ቢሰጥ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ ውርስን የሚመለከት ሲሆን የወራሽነት ማስረጃ ማውጣት ተፈጻሚ በሚሆነው የይርጋ ድንጋጌ ተፈጻሚነት ላይ ያለውን ውጤት የሚመለከት ነው፡፡ አመልካቾች የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው የተደረገ ክርክር ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካቾች ከሳሾች፣ ተጠሪ ተከሳሽ ሆነው ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾች ግንቦት 02 ቀን 2014 ዓ/ም ጽፈው ባቀረቡት ክስ የሟች እናታቸው ሟች እማሆይ አሰለፍ ኃይሌ የውርስ ሀብት የሆነው የገጠር መሬት ለመካፈል ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸው እናታችን የሞቱት መስከረም 14 ቀን 2011 ዓ/ም ነው፣ ክሱ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ ሲታሰብ ሦስት ዓመት ከሰባት ወር ስለሚሆን ክሱ በፍ/ሕ/ቁ. 1000(1) መሠረት በሦስት ዓመት ይርጋ ቀሪ ነው በማለት የይርጋ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡

የሥር ወረዳ ፍርድ ቤት በይርጋ መቃወሚያው ላይ ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ሟች እናታቸው መስከረም 14 ቀን 2011 ዓ/ም የሞቱ ሲሆን ተጠሪ ንብረቶችን ከዚህ ጊዜ ጀምሮ መያዛቸው በማስረጃ ተረጋግጧል፣ ክሱ እስከቀረበበት ግንቦት 02 ቀን 2014 ዓ/ም ድረስ ያለው ጊዜ ሲቆጠር ሦስት ዓመት ያለፈው በመሆኑ ክሱ በፍ/ሕ/ቁ. 1000(1) መሠረት በሦስት ዓመት ይርጋ ቀሪ ነው በማለት ወስኗል።የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ሰበር ችሎት የአመልካቾችን የይግባኝና የሰበር አቤቱታ ባለመቀበል ሰርዘዋል።

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው። አመልካቾች መጋቢት 4 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይህን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ሲሆን ይዘቱም፡-የአመልካቾች ወላጅ እናት እማሆይ አሰለፍ ኃይሌ በሞት የተለዩት መስከረም 14 ቀን 2011 ዓ.ም ሲሆን አመልካቾች ወራሽነታችንን በደላንታ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 0124410 በቀን 03/03/2012 ዓ.ም በአንድ አመት ጊዜ ዉስጥ አረጋግጠናል፣ አመልካቾች እናታችን ከሞተች ግዜ ጀምሮ በ3 ወር ጊዜ ውስጥ ወራሽነታችንን ያሳወጅን በመሆኑ ወራሽነቱን በ 3 አመት ግዜ ዉስጥ ያሳወጀ ወራሽ ደግሞ ክስ ሳይመስርት 3 አመት አልፎታል ተብሎ የይርጋ መቃወሚያ ሊነሳበት እንደማይችል የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በተለያዩ መዝቦች ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠበት በመሆኑ የ3 አመት ይርጋ ተፈጻሚ ሚሆነው በ3 አመት ጊዜ ዉስጥ ወራሽነቱን ላላረጋገጠ ወራሽ ነው። ክርክር የተነሳበትን የውርስ መሬት ደግሞ መጀመሪያ ይዞት የነበረው ተጠሪ ሳይሆን የስር 3ኛ ከሳሽ የሆነው መኩሪያ ደምሴ ነበር፣በኋላ ግን ተጠሪና የስር 3ኛ ተከሳሽ በሌላ መዝገብ እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ተከራክረው በሰ/መ/ቁ 0331598 ውሳኔ የተሰጠው የካቲት 1 ቀን 2014 ዓ.ም ሲሆን ተጠሪም ይህን መሬት የያዘው ይህን ፍርድ ካገኘበት ከዚህ ከየካቲት 1 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ ነው፣ አመልካቾች በስር ደላንታ ወረዳ ፍርድ ቤት ክስ የመሰረትነው ደግሞ በቀን 02/09/2014 ሲሆን ተጠሪ አከራካሪውን መሬት በፍርድ ያገኘበትና እና አመልካቾች ክስ የመሰረትንበት የጊዜ ልዩነት ሲቆጠር 4 ወር ብቻ በመሆኑ ተጠሪ መሬቶቹን የያዘው ሟች ከሞተችበት እለት ጀምሮ እንደሆነ በመቁጠር ክሱ በይርጋ ታግዷል በማለት የተሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፣ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊታረም ይገባል የሚል ነው።

የሰበር ሰሚው ችሎትም የአመልካቾችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ አመልካቾች የወራሽነት መብታቸውን በህግ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ያረጋገጡ መሆናቸውን ፤ እንዲሁም አከራካሪው ይዞታና ንብረት በተጠሪ እጅ የገባው የአመልካቾች እናት እንደሞቱ ሳይሆን ከውሳኔ በኃላ ነው በሚል ያቀረቡት ክርክር ታልፎ የዳኝነት ጥያቄያቸው በይርጋ ይታገዳል ተብሎ የተሰጠው ብይንና ውሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር መዝገብ ቁጥር 44237 እና በሌሎች ተመሳሳይ መዛግብት የተሰጠውን ትርጉም እንዲሁም ህጉን የተከተለ መሆን አለመሆኑን አጣርቶ ለመወሰን ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ ታዟል።

ተጠሪ ነሀሴ 5 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጡት መልስ ይዘትም፡- በስር ፍርድ ቤቶች በተደረገው ክርክር ክርክር የተነሳበትን ይዞታና ንብረት ተጠሪ እጅ የገባው ሟች እናትን እንደሞቱ ሳይሆን ተጠሪ ከስር 3ኛ ተከሳሽ ጋር እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ድረስ ተከራክረው ውሳኔ ከተሰጠ ከየካቲት 1 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ ነው በሚል በስር ፍርድ ቤት ያላቀረቡት አዲስ መከራከርያ ከመሆኑም በላይ ግራ ቀኞችን በስር ፍርድ ቤት ያቀረብናቸው ምስክሮች አከራካሪውን ይዞታና ንብረት እናታችን ከሞተችበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረሥ ይዤው የምጠቀምበት ተጠሪ ስለመሆኔ መስክረዋል፣ አመልካቾች ያቀረቡት ክስ በወራሾች መካከል የተነሳ ክርክር በመሆኑ እና ክሱ የቀረበው ሟች ከሞቱ ከ3 ዓመት ከ7 ወር በኂላ በመሆኑ በ 3 ዓመት ይርጋ ቀሪ የሚሆን ነው፣ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የወራሽነት ማስረጃ አስቀድሞ ማውጣት የውርስ ንብረቱን ለመረከብ ወይም ለመከፋፈል የሚቀርብ ክስ በይርጋ መብቱ ሳይታገድ በማናቸውም ጊዜ ለማቅረብ የሚያስችል ሕጋዊ ውጤት ያለው መሆን አለመሆኑን ከተገቢው ሕግ ጋር በማገናዝብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

እንደመረመርነው አመልካቾች ያቀረቡት ክስ ተጠሪ የሟች እናታችን የገጠር መሬት ስለያዙ እንዲያካፍሉን ይወስንልን በማለት ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን ተጠሪ የይርጋ መቃወሚያ እና ፍሬ ነገር ክርክር አቅርበዋል፤ የይርጋ ክርክሩ የቀረበው አመልካች ክሱን ለማቅረብ የክስ የማቅረቢያ ጊዜው አልፏል በሚል ነው፡፡ ይርጋ መብትን (extinctive prescription) እና መብትን ለማስከበር የሚቀርብ ክስን በጊዜ ገደብ ቀሪ የሚያደርግ (limitation of action) ነው፡፡ እንደክሱ መሠረት ዓይነት ተፈጻሚ የሚሆነው የይርጋ ደንብና ሕግ የተለያየ ነው፡፡ የቀረበዉ ክስ በይርጋ ቀሪ ሊሆን የሚገባ መሆን አለመሆኑን በመወሰን ረገድ ፍርድ ቤቶች መሰረት እንዲያደርጉ የሚጠበቅባቸዉ በከሳሽ ክስ ላይ የተመለከተዉን የክስ ምክንያት እንጂ ተከሳሽ ለይርጋዉ መሰረት ይሆናል በማለት በበኩሉ ያቀረበዉን ሌላ የክርክር ምክንያት አለመሆኑንም መገንዘብ ያስፈልጋል፤የቀረበው ጉዳይ ከገጠር እርሻ መሬት ይለቀቅልኝ ክስ ነው፡፡ ሁሉም የገጠር የእርሻ መሬት ጋር የተያያዘ የክስ ዓይነት ላይ ተመሳሳይ የይርጋ ደንብ ተፈጻሚ ሊሆን አይችልም፡፡ ክሱ ይዞታ እንዲለቀቅ የሚቀርብ የይዞታ መብትን ለማስከበር የሚቀርብ ክስ ወይም የገጠር መሬት ውርስ ይገባናል በሚል የቀረበ ክስ ወይም ከገጠር መሬት ጋር የተያያዘ ውልን መሠረት ያደረገ ክስ መሆኑ እየታየ እንደክሱ የዳኝነት መሠረት ክሱ በይርጋ ቀሪ የሚሆንበት ጊዜና ለጉዳዩ ተፈጻሚ የሚሆነው የይርጋ ደንብ ወይም ድንጋጌ የተለያየ ነው፡፡ ስለሆነም የክሱን መሠረት መለየት የይርጋ ክርክሩንም ሆነ ቀጣይ ያሉ ሂደቶችን ለመመራት አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

የአመልካቾች ክስ በሌላ ወራሽ የተያዘን የውርስ ይዞታ ለመካፈል የቀረበ ነው፣ ለዚህ ክስ ተፈጻሚነት ያለው የይርጋ ደንብ በፍ/ሕ/ቁ. 1000(1) የተመለከተው የሦስት ዓመት ጊዜ ይርጋ ነው፡፡ የግራቀኙ ሟች እናታቸው እማሆይ አሰለፍ ኃይሌ መስከረም 14 ቀን 2011 ዓ/ም የሞቱ ሲሆን ተጠሪ ንብረቶችን ከዚህ

ጊዜ ጀምሮ መያዛቸው በሥር ፍርድ በማስረጃ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፣ ፍሬ ነገርን በማስረጃ ለማጣራትና ማስረጃ ለመመዘን ሥልጣን የተሰጠው ፍርድ ቤት ያረጋገጠው ፍሬ ነገር መሠረታዊ የሕግ ስህተት የመመርመር ሥልጣን ብቻ ባለው ሰበር ችሎት ላይ ክርክር ሊቀርብበት አይችልም፤ ክሱ እስከቀረበበት ግንቦት 02 ቀን 2014 ዓ/ም ድረስ ያለው ጊዜ ሲቆጠር የሦስት ዓመት ጊዜ ያለፈው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

አመልካቾች የወራሽነት ማስረጃ አስቀድመው ያወጡ መሆኑን በመግለጽ ክሱ በይርጋ ሊታገድ አይገባም በማለት ሰበር ሰሚ ችሎቱ በሰበር መዝገብ ቁጥር 44237 እና ሌሎች መዛግባት ላይ የሰጠውን ትርጉም መሠረት አድርገው ተከራክረዋል፡፡ የወራሽነት የምስክር ወረቀት መያዝ ወራሽ ተደርጎ ከመገመት ባለፈ የንብረት መብት የማይፈጥር መሆኑ፣ የውርስ ንብረት ጥያቄ ሲቀርብ የወራሽነት ማስረጃ መያዝ አለመያዝ ልዩነት ሳይኖረው በፍ/ሕ/ቁ. 1000(1) መሠረት የሶስት ዓመት ጊዜ ውስጥ የወራሽነት ጥያቄ ካልቀረበ ክሱ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑና የሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 205248 (መ/ቁ. 44237፣38533 ወዘተ) የወራሽነት የምስክር ወረቀት የያዘ ሰው በማንኛውም ጊዜ የውርስ ንብረት ጥያቄ ማንሳት ይችላል በማለት የሰጠው ትርጉም በሰበር መዝገብ ቁጥር 243973 ላይ በሰባት ዳኞች ተለውጧል፡፡ በተሰጠው አዲስ ትርጉም መሠረት የውርስ ማጣራት ተጠናቆ ንብረቱ የጋራ ባልሆነበት ሁኔታ የወራሽነት ምስክር ወረቀት በመያዝ ብቻ የፍ/ሕ/ቁ. 1062 መሰረት በማድረግ ያለጊዜ ገደብ የክፍፍል ጥያቄ ሊነሳ አይችልም፡፡

በመሆኑም አመልካቾች የወላጅ እናታቸው ሟች እማሆይ አሰለፍ ኃይሌ የውርስ ሀብት የሆነውን የገጠር መሬት ለመካፈል ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን ተጠሪ ክሱ በፍ/ሕ/ቁ. 1000/1/ መሠረት የሦስት ዓመት ጊዜ ካለፈው በኋላ የቀረበ ክስ በመሆኑ ይርጋ የታገደ ነው ሲሉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ አመልካቾች የወራሽነት ምስክር ወረቀት ያወጡ ቢሆንም የውርስ ሀብቱን በመያዝ አልተጠቀሙበትም፣ የውርስ ሀብቱ ከተጠሪ ከተያዘ ሦስት ዓመት ያለፈው ስለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም የቀረበው የውርስ ንብረት ክፍፍል ክስ በፍ/ሕ/ቁ. 1000/1/ መሠረት በሦስት ዓመት ጊዜ ገደብ በይርጋ ቀሪ ነው ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ሕጉን የተከተለ በመሆኑ የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አላገኘንበትም፤ ስለሆነም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 0336925 የካቲት 16 ቀን 2015 ዓ/ም፣ የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 57366 ሕዳር 23 ቀን 2015 ዓ/ም እና የደላንታ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 0131757 ጥቅምት 07 ቀን 2015 ዓ/ም አመልካቾች አስመልክቶ የሠጡት ውሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1)(ሀ) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. ግራቀኙ በዚህ ችሎት ክርክር የደረሰባቸውን ወጭና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ት<u>ዕዛዝ</u>

1. የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
2. በዚህ ችሎት ሐምሌ 20 ቀን 2015 ዓ/ም ክርክር እንዲታገድ የተሰጠው ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ
3. መዝገቡ ተዘግቷል ወደመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የዉዝፍ መዛግብት ሰበር ችሎት

**የሰበር መ/ቁ 243976**

**ጥቅምት 04 ቀን 2017 ዓ/ም**

**ዳኞች:-** ሽመክት አሰፋ

ገበየሁ ፈለቀ

ዓለማየሁ ሹናራ

ተናኘ ጥላሁን

ዘዉዲቱ ታደሰ

አመልካች፡- ሻምበል አዱኛ መገርሳ አልቀረበም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ፀሐይ ደምሴ አልቀረቡም

መርምረን ፍርድ ሰጥተናል ፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ ከመኖሪያ ቤት ሽያጭ ውል ጋር የተያያዘ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን በስር ፍርድ ቤት የአሁን የሰበር አመልካች ተከሳሽ የነበሩ ሲሆን የሰበር ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ ነበሩ ፡፡

ተጠሪ ለሉሜ ወረዳ ፍ/ቤት በቀን 22/03/2014 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት ክስ የአሁን አመልካች በሞጆ ከተማ ቀበሌ 01 ዉስጥ የሚገኘዉን ካርታ ቁጥሩ 2801/2000 የሆነዉ እና በ160 ካ.ሜ

ላይ ያረፈዉ መኖሪያ ቤት በተወካዩ በኩል መስከረም 01 ቀን 2005 ዓ/ም ብር 460,000.00(አራት መቶ ስልሳ ሺ) ብር ሸጦልኝ ይህ የሸጠው ቤት በመንገድ ልማት ምክንያት ተወስዶብኝና ፈርሶ ካሳ ተሰጥቶኝ በእጄ ያለኝ ሲሆን ከሳሽ የተሰጠኝን ምትክ የቦታ ስም ለማዛወር የማልችል ስለሆነ የተከሳሽ ተወካይን ስጠይቅ ዉክልናዋ የተነሳ በመሆኑ ማዛወር ስለማትችል ተከሳሹን አዛዉርልኝ ስለዉ ፈቃደኛ ሲሆን ስላልቻለ በውላችን መሰረት ተገዶ ስም እንድያዞርልኝ እንዲያደርግ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

የአሁን አመልካች በወረዳው ፍርድ ቤት ባቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና በዋናው ጉዳይ ላይ በሰጡት መልስ የአሁን ከሣሽ ለክርክር ምክንያት የሆነው ቤት የተከሣሽ ተወካይ ከሆነችው ወ/ሮ ትግስት ታምሩ ላይ በቀን 28/01/2005ዓ.ም በብር 460,000/አራት መቶ ስልሳ ሺህ ብር / ገዛው የምትለው ሐሰት ነው ምክንያቱም በቀን 25/01/2005 በተፈፀመ ሽያጭ ውል በብር 460,000 የእኔ ተወካይ ወ/ሮ ትግስት ታምሩ ከእኔ ላይ የገዛችዉ ስለሆነ ይህ ክርክር ያስነሳው ቤት የእሷ ስለሆነ ይህንን ቤት ለከሣሽ መሸጥ የሚገባት በራሷ ስም ነው እንጂ በስሜ አይደለም ፤ በሰጠኋት ውክልና ንብረቴን ከሕግ ውጭ ለራሷ ለማድረግ ጥረት አድርጋ ሊሳካላት ስላልቻለ መጨረሻ ደረጃ ለማድረስ የአሁን ከሣሽ ከእኔ ተወካይ ጋር የሐሰት ውል በማዘጋጀት በወ/ሮ ትግስት ታምሩ በመዝገብ ቁጥር 93421 ላይ ክስ አቅርባ የነበረውን ከሣሽ እንዳለ ገልብጣ በሐሰት ያቀረበችው ክስ ስለሆነ ውድቅ እንዲሆንልኝ ፤ከሣሽ የካርታ ቁጥር 2001/2000 የሆነ ቤት ላይ ካሣ ተከፍሎኛል ያለችው ሐሰት ነው፡፡ ምክንያቱም ከሣሽ ከክሷ ጋር አያይዛ ያቀረበችው የግዥ እና ሽያጭ ውል ጀምር ውል ስልጣን ባለው አካል ቀርቦ ተረጋግጦ የስም ዝውውር ሳይፈፀም በተከሣሽ ስም እያለ ለእሷ ካሣ የሚከፈልበት ምክንያትም ሆነ ለእሷ የሚስጠት ምትክ ቦታ የለም፡፡ ከሣሽ ተከሣሽ ስም እንዲያዛውርልኝ ጠይቄው እንቢ አለኝ የምትለው ከእውነት የራቀ ነው የሚል ይዘት ያለው ክርክር አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የሎሜ ወረዳው ፍርድ ቤት የካርታ ቁጥር 2801/2000 ተመዝግቦ ያለ በከሣሽ እና በተከሣሽ ተወካይ መካከል የተደረገው የግዥ እና ሽያጭ ውል አለ? ለሚለውን ጭብጥ ይዞ  የከሣሽ ምስክሮች በሰጡት ቃል መሰረት በማድረግ ተወካይ የሆነችው ወ/ሮ ትግስት ታምሩ ከምትባል ሴት ላይ በብር 460,000/አራትሺህ /ብር ለመግዛት የይዞታ ማረጋገጫ በእጇ አድርሳ ገንዘቡን ለተከሣሽ ተወካይ ሰጥታ ቦታው ከወሰደች በኂላ ደግሞ ይህ ከሣሽ የገዛችው ቦታ ወደ ስሟ ሳይዛወር መንገድ ወጥቶበት የቦታው ምትክ መጥቶ ቦታውን በእጇ አድርጋ የቦታውንም ካሣ የተቀበለች መሆኑን ፤ይህ ደግሞ የመነጨው በቀን

28/01/2005 በከሣሽ እና በተከሣሽ ተወካይ መካከል በተደረገ ውል መሆኑን ስለዚህ ይህ ውል ከሣሽ እና የተከሣሽ ተወካይ መካከል የተደረገ ህጋዊ የሆነ ውል በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1731 እንደሚገልፀው በሰዎች መካከል ያለ ስምምነት ሕግ እንደሆነ እና በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2005/1/ ስርም ይህ የቀረበው የፁሁፍ ማስረጃ የሚታመን ማስረጃ መሆኑን ስለዚህ በቀን 28/01/2005 የተከሣሽ ተወካይ የሆነችው ወ/ሮ ትግስት ታምሩ እና የአሁን ከሣሽ መካከል የተደረገ የግዥ እና የሽያጭ ውል የውክልና ስልጣን የተከሣሽ ተወካይ በቀን 25/01/2005 የተደረገ ሲሆን ተከሣሽም ለተወካዩ አሁን ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት እንድትሸጥ ስም ማዛወር እንድትችል ሙሉ የውክልና ስልጣን መስጠቱን አልካደም ተወካይዋ የቤት ሽያጭ ዉሉን ፈፀመችው በሰበር አመልካች የተሰጣት የውክልና ስልጣኗ ሳይነሳ በፊት ሲሆን አሁን ዉክልናዋ በሰበር አመልካች የተነሳ በመሆኑ እና ስም ማዛወር ስለማትችል ለሰበር ተጠሪ የተሰጠዉን ምትክ ቦታ  በቀን 16/11/2013 በወኪሉ ዓማካኝነት በተደረገዉ የሽያጭ ውል መሰረት የሰበር አመልካች የቤቱን ስም ሀብት ለአሁን የሰበር ተጠሪ እንዲዛወር ሊያደርግ ይገባል በማለት ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁን አመልካችም በየደረጃው ባሉ የክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች ማለትም ለምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ፣ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡት ቅሬታ የወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔውን በማጽናት ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡

አሁን ያቀረቡት የሰበር አቤቱታም እነዚህ በክልሉ ሁሉም ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ውሳኔዎች መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸው ናቸው በሚል ነው፡፡  ይዘቱም በአጭሩ፡- ተጠሪ በሉሜ ወረዳ ፍ/ቤት በመሠረተችዉ ክስ ከአመልካች ተወካይ ቤት ገዝቼ መንግስት የቤቱን ቦታ ለልማት ፈልጎ ካሳም ተከፍሎኝ ተለዋጭ ቦታም ተሠቶኝ  የአዉኑ አመልካች ስም ሊያዛዉርልኝ ፍቃደኛ ስላልሆነ ተገዶ ስም እንድያዞሪልኝ እንድወሰንልኝ የሚል ክስ ነዉ፡፡ ስለዚህ የተጠሪ ጥያቄ የዉል ይፈጸምልኝ ጥያቄ ሳይሆን የስም ይዛወርልኝ ጥያቄ ነዉ፡፡ ይህ ደግሞ ለአስተዳደር አካላት የሚቀርብ እንጅ በፍርድ ቤት የሚታይ አለመሆኑ  ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በተመሳዳይ ጉዳይ  በሰ/መ/ቁ ቁ. 49428 እና በሰ/መ/ቁ. 33945 ገዥ ዉሳኔ የሰጠበት ነዉ ፡፡ስለሆነም የስም ይዛወሪልኝ ጥያቄ የክስ ምክንያት (cause of action) የለዉም ተብሎ ሊወሰወን የሚገባዉ ነዉ፡፡ ተጠሪ ያቀረበችዉ የቤት የሽያጭ ዉል ዉል ለማዋዋል ስልጣን ያለዉ አካል ፊት ቀርቦ የጸደቀ ዉል ባለመሆኑ

የተካደ በመሆኑ ዉል መሆኑ ቀርቶ በረቂቅ ደረጃ ሆኖ እንደሚቀር እና በተዋዋዮች መካከልም አንዳች የምፈጥረዉ የህግ ግደታ እንደለሌ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 21448 ተሰጥቷል፡፡ በዚህ አስገዳጅ ዉሳኔ መሠረትም ተፈጻሚል የተባለዉ ዉል በእኔ እና በተጠሪ መካከል አንዳችም የምፈጥረዉ የህግ ግዴታ የለዉም በመሆኑም በየደረጃዉ ያሉ የኦሮሚያ ክልል ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ መሰረታ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ ነዉ የሚል ይዘት ያለዉ ነዉ፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎቱ በዚህ ጉዳይ ምንም እንኳ አመልካች ቤትና ቦታ ለመሸጥ የሚያስችል ውክልና ስልጣን ተጠሪ ቤቱን ሽጣልኛለች ላለችው ግለሰብ መስጠቱ ግራ ቀኙን ያላከራከረ እና ይህ ፍሬ-ነገር በማስረጃ ጭምር የተረጋገጠ ቢሆንም በሌላ በኩል ግን ይህ ለክሱ መነሻ የሆነዉ ቤቱ ሽያጭ ዉል ስለመኖሩ በአመልካች (በወካይ) እስከተካደ (ምንም እንኳ በተወካይ በኩል የታመነ ቢሆንም) እና ዉሉም ከፍ/ብ/ህ/ቁ.1723 ድንጋጌ አንፃር በዉል አዋዋይ ፊት ያልተደረገ ከመሆኑ ጋር ጉዳዩ ተገናዝቦ ሲታይ አመልካች በሽያጭ ዉሉ መሰረት ሊገደድ ይገባል ሲሉ የስር ፍ/ቤቶች የደረሱበት መደምደሚያ ተገቢት ያለዉ መሆን አለመሆኑን ግራ ቀኙ ባሉበት መርምሮ ተገቢዉን ለመወሰን ሲባል የሰበር አቤቱታዉ ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ቀርቦ ሊታይ ይገባል ተብሎ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር አድርገዉበታል ፡፡

ተጠሪ ቀርበው የሰጡት መልስ ይዘት በአጭሩ፡- ለክርክሩ መነሻ የሆነው የሽያጭ ውል በአመልካቹ ህጋዊ ወኪል በኩል በቀን 28//2005 የተደረገ ውል ቢሆንም ውሉ ለመደረጉ በተወካዩ የታመነ ስለሆነ እና በእራሱ በአመልካች እንደተፈፀመ የሚቆጠር በመሆኑ ይህ ፌዴራል ጠቅላይ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ በ36887 በሰጠው ገዥ ትርጉም መሰረት ውሉ ስልጣን ባለው አካል ፊት አልተመዘገበም በማለት መቃወም ስለማይችል ክርክሩ ተቀባይነት የለዉም፡፡ አመልካች ከተወካዩ ጋር አለመግባባት በመፍጠሩ ምክንያት ዉክልናዉን በማንሳቱ በውሉ መሰረት ለመፈፀም ባለመቻሉ በውሳችን መሰረት ተገዶ እንዲፈፅምልኝ የሚል ክስ ስለሆነ ይህ ደግሞ ህገ መንግስታዊ መብት ስለሆነ የአሁኑ አመልካች በውሉ መሰረት ይፈጽም መባሉ  ተገቢ ነዉ፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶችም የሰጡት ዉሳኔ አግባብነት ያለዉ ስለሆነ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠ ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለውም ተብሎ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 82234 በሰጠው ገዥ ትርጉም መሰረት እንዲፀናልኝ እጠይቃለሁ የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡

የሰበር አመልካችም የሰበር ቅሬታዉን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርቦ ክርክሩ ተጠቃሏል፡፡ አጠቃላይ የክርክሩ አመጣጥ እና ይዘቱ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን እኛም ቅሬታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ ፣በስር ፍርድ ቤት ከተደረገዉ ክርክር ፣የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እንዲሁም ለጉዳዩ አግባብነት ካለዉ ህግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነዉም ቅሬታዉ ያስቀርባል ሲባል የተያዘዉ ጭብጥ ምንም እንኳ አመልካች ቤትና ቦታ ለመሸጥ የሚያስችል የውክልና ስልጣን ተጠሪ ቤቱን ሸጣልኛለች ላለችሁ ግለሰብ መስጠቱ ግራ ቀኙን ያላከራከረ እና ይህ ፍሬ-ነገር በማስረጃ ጭምር የተረጋገጠ ቢሆንም በሌላ በኩል ግን ይህ ለክሱ መነሻ የሆነዉ ቤቱ ሽያጭ ዉል ስለመኖሩ በአመልካች (በወካይ) እስከተካደ (ምንም እንኳ በተወካይ በኩል የታመነ ቢሆንም) እና ዉሉም ከፍ/ብ/ህ/ቁ.1723 ድንጋጌ አንፃር በዉል አዋዋይ ፊት ያልተደረገ ከመሆኑ ጋር ጉዳዩ ተገናዝቦ ሲታይ አመልካች በሽያጭ ዉሉ መሰረት ሊገደድ ይገባል ሲሉ የስር ፍ/ቤቶች የደረሱበት መደምደሚያ ተገቢት ያለዉ መሆን አለመሆኑን አጣርቶ ለመወሰን ሲሆን ከዚሁ ጭብጥ አንጻር እንደመረመርነዉ በእርግጥ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 21448 በአዋዋይ ፊት ያልተደረገ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ዉል ፈራሽ እንደሆነ ገዥ ዉሳኔ መስጠቱ ግልጽ ነዉ፡፡ ይሁን እና ዉሉ በተከራካሪ ወገኖች ካልተካደ ግን በዉል አዋዋይ ፊት የተደረገ ዉል አይደለም በሚል ብቻ ዉሉ ፈራሽ ሊሆን እንደማይችል በሰ/መ/ቁ 36887 ሌላ ገዥ ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡ በአሁኑ ጉዳይ የሰበር አመልካች አከራካሪዉን ቤት ለመሸጥ የሚያስችል የዉክልና ስልጣን ቤቱን ለሸጠችዉ ወ/ሮ ትግስት ታምሩ መስጠቱ በስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ነዉ፡፡ ወኪሉም ይህንን ቤት አልሸጥኩም አላለችም ይህ ከሆነ ደግሞ ወኪል የሰራዉ ስራ በተሰጠዉ የዉክልና ስልጣን ልክ እስከሆነ ድረስ በወካዩ እንደተሰራ የሚቆጠር መሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ 2189(1) ድንጋጌ ስር የተመለከተ ስለሆነ የሰበር አመልካችም በወኪሉ ዓማካኝነት የተፈጸመዉን የሽያጭ ዉል በዚሁ ድንጋጌ መሰረት እንዳመነ የሚቆጠር ነዉ ፡፡ከዚህ በተጨማሪ የሰበር አመልካች በአንድ በኩል በቀን 25/01/2005 በተፈፀመ ሽያጭ ውል በብር 460,000 የእኔ ተወካይ ወ/ሮ ትግስት ታምሩ ከእኔ ላይ የገዛችዉ ስለሆነ ይህ ክርክር ያስነሳው ቤት የእሷ ስለሆነ ይህንን ቤት ለከሣሽ መሸጥ የሚገባት በራሷ ስም ነው እንጂ በስሜ አይደለም በማለት በወረዳዉ ፍርድ ቤት ክርክር ማቅረቡን የተመለከትን ሲሆን ይህ የሚያሳየዉ ክርክሩ ወጥነት የሌለዉ እና እምነት የሚጣልበት አለመሆኑን ነዉ ፡፡ በሌላ በኩል የስም ይዛወርልኝ ጥያቄ የፍርድ ቤት ስልጣን አይደለም በማለት በሰበር አመልካች የተነሳዉን ክርክር በተመለከተ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 82234 ሽያጭ በዉሉ መሰረት የቤቱን ስመ ንብረት የሚመለከተዉ አካል ወደ ገዥዉ ለማዞር እንዲችል በሚመለከተዉ ክፍል ቀርቦ ተገቢዉን እንዲፈጽም በማለት ገዥ የሚያቀርበዉ ክስ የክስ ምክንያት የለዉም ሊባል እንደማይችል እና በፍርድ ቤትም ታይቶ ሊወሰን እንደሚችል ገዥ ዉሳኔ የሰጠበት ሰለሆነ እና በአሁኑ ጉዳይም የተነሳዉ ክርክር ከዚሁ ጋር ተመሳሳይ በመሆኑ ለዚህ ጉዳይም ተፈጻሚነት ያለዉ ስለሆነ አመልካች በዚህ ረገድም ያነሳዉ ክርክር ተቀባይነት የሌለዉ ነዉ፡፡

በመጨረሻም የሰበር ቅሬታ የቀረበበት ዉሳኔ የተሰጠዉ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሲሆን ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታዉን ተቀብሎ በሰበር የማየት ስልጣን የሚኖረዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ የሚቃረን ሲሆን እንዲሁም አግባብነት የሌለዉን ህግ በመጥቀስ ወይም ህግን ያላግባብ በመተርጎም የተሰጠ ሆኖ ጉዳዩም አገራዊ ፋይዳን የሚመለከት ሲሆን ብቻ ስለመሆኑ የአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 (1/ሐ/ እና /መ) ድንጋጌዎች እና ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ለእነዚሁ ድንጋጌዎች በሰ/መ/ቁ/ 208655 የሰጠዉ ገዥ ዉሳኔ ያስገነዝባል፡፡

አሁን በያዝነዉ ጉዳይም ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ ጉዳይ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ ሲሆን የዉሳኔዉ ይዘት በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 (1/ሐ/እና /መ) ስር ከተመለከቱ ድንጋጌዎችእና ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 208655 ከተሰጠዉ ገዥ ዉሳኔ አንጻር ሲታይ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሰረታዊ የሆነ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡

በመሆኑም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ዉሳኔ

በሎሜ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 94118 ሚያዚያ 10 ቀን 2014 ዓ/ም ተሰጥቶ በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 67809 ግንቦት 05 ቀን 2014 ዓ/ም በትዕዛዝ ፤በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 400046 ጥቅምት 02 ቀን 2015 ዓ/ም እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 406631 ታህሳስ 18 ቀን 2015 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት የጸናዉ ፍርድ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለበትም ተብሎ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡

የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

በዚህ ችሎት ተሰጥቶ የነበረዉ የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል ለሚመለከተዉ ክፍል ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ/ጋ

የሰ/መ/ ቁጥር 244052

ጥቅምት 07 ቀን 2017 ዓ/ም

ዳኞች - ተፈሪ ገብሩ (ደ/ር)

እንዳሻዉ አዳነ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሰናይት አድነዉ

ሀፊዝ አባጀማል

አመልካች ፡-በከልቻ ትራንስፖርት አ/ማ - ጠበቃ ታደሰ ገመቹ - ቀረቡ

ተጠሪ ፡- የኢትዮጵያ ስኳር ኢንዱስትሪ ግሩፕ (የቀድሞ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ስኳር ኮርፖሬሽን)-አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከለታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ የጭነት ማጓጓዣ አገልግሎት ዉልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረዉ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረበው ክስ ነው፡፡

አመልካች ባቀረበው ክስ ከተጠሪ ጋር 360,000 (ሶስት መቶ ስድሳ ሺ) ኩንታል ስኳር ከጂቡቲ ወደብ ወደ አዲስ አበባ፣ አዳማ፣ ወንጂ እና መተሐራ የስኳር መጋዘኖች ለማድረስ መስከረም 06 ቀን 2012 ዓ/ም በተዋዋልንዉ ዉል መሰረት ስኳሩን በማጓጓዝ የዉል ግዴታችን የተወጣሁ ቢሆንም ተጠሪ በዉሉ መሰረት ሊከፍል የሚገባዉን ክፍያ ያልከፈለ በመሆኑ ተጠሪ መክፈል ከነበረበት የአገልግሎት ክፍያ ዉስጥ ያልከፈለውን ብር 984,871.00 (ዘጠኝ መቶ ሰማንያ አራት ሺ ስምንት መቶ ስባ አንድ)፤ ለመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና የተያዘ ገንዘብ ብር

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

1,844,233.00 (አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ አርባ አራት ሺ ሁለት መቶ ስላሳ ሶስት) እና ተጠሪ በቂ ማከማቻ ቦታ እና ሰራተኛ ባለማዘጋጀቱ ለደረሰብን የግዜ ብክነት ኪሳራ ብር 1,480,040.00 (አንድ ሚሊዮን አራት መቶ ሰማንያ ሺ አርባ) እንዲከፍል ይወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ተጠሪ በሰጠው መልስ አመልካች ለሰጠዉ አገልግሎት ሙሉ ክፍያ ፈፅመናል፤ አመልካች የነበረው ቀሪ ክፍያ ስኳሩን በወቅቱ ባለማንሳቱ የአራት መርከቦች ዲሜሬጅ ክፍያ ብር 984,871.00 (ዘጠኝ መቶ ሰማንያ አራት ሺ ስምንት መቶ ሰባ አንድ) የተከፈለ በመሆኑ ቀሪ ክፍያ የለብንም፤ የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ገንዘቡን በተመለከተም የአመልካች የፋይናንስ ክፍል ፈርመዉ የተቀበሉ እና የተመለሰላቸዉ በመሆኑ ልንጠየቅ አይገባም፤ የአመልካች ተሽከርካሪዎች የግዜ ብክነት ያልደረሰባቸዉ በመሆኑ እና ደርሷል ቢባል እንኳን በአመልካች ምክንያት እንጂ በተጠሪ ምክንያት ካለመሆኑም በላይ ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ ልንጠየቅ አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ ባደረጉት ዉል አንቀፅ 4(8) መሰረት የዲሜሪጅ ክፍያ የመክፈል ግዴታ የአመልካች በመሆኑ ጥያቄዉ ተቀባይነት የለዉም፤ በወቅቱ ስኳሩን ከመርከብ ላይ እንዲወርድ ባለማድረጉ የአራት መርከቦች ዲሜሬጅ ብር 2,289,108.00 (ሁለት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሰማንያ ዘጠኝ ሺ አንድ መቶ ስምንት) አመልካች የከፈለ ቢሆንም በተገቢዉ ግዜ ቢከፈል ኖሮ የዲሜሪጁ እዳዉ 61,795.01 ዶላር ወይም በወቅቱ ምንዛሬ ብር 1,959,519.45 (አንድ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሃምሳ ዘጠኝ ሺ አምስት መቶ አስራ ዘጠኝ ከ45/100) የሚሆን በመሆኑ ተጠሪ ልዩነቱን ከእነ ወለዱ ብር 330,487.55 (ሶስት መቶ ስላሳ ሽ አራት መቶ ሰማንያ ስባት ከ55/100) እንዲከፍል፤ እንዲሁም ለመልካም ስራ አፈፃጸም የተያዘን ገንዘብ በተመለከተ ለሂሳብ ባለሙያቸው ለአቶ ተመስገን አዲሴ ከፍለናል በማለት መታወቅያዉን ኮፒ አድርጎ ከማቅረብ ዉጭ መክፈሉን የሚያረጋገጥ ማስረጃ ያላቀረበ በመሆኑ ለመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ገንዘብ ብር 1,844,233 (አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ አርባ አራት ሺ ሁለት መቶ ስላሳ ሶስት) ሊከፍል ይገባል፤ በአጠቃላይ ተጠሪ ብር 2,174,720.55 (ሁለት ሚሊዮን አንድ መቶ ስባ አራት ሺ ስባት መቶ ሃያ ከ55/100) ለአመልካች ይክፈል በማለት ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ ላይ የአሁን ተጠሪ ይግባኝ እንዲሁም አመልካች መስቀለኛ ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራቀኙን ቅሬታ አስቀርቦ ክርክራቸውን ከሰማ በኃላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በማሻሻል በሰጠው ውሳኔ የአመልካች የመጨረሻ የዲሜሪጁ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

እዳ 61,795.01 ዶላር መሆኑ ተረጋግጧል፤ የዲሜሪጂ ክፍያ መጠኑ ከፍ ያለዉ ተጠሪ በዉጭ ምንዛሬ ወዲያዉኑ ክፍያ ባለመፈፀሙ በግዜ ሂደት በተከሰተ የምንዛሬ ለዉጥ መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን በዚህ ረገድ ተጠሪ ያቀረበዉ ማስተባበያ ክርክር የለም፤ ይሁን እንጂ የስር ፍርድ ቤት በቀን 07-09-2012 ዓ/ም በነበረዉ የዶላር ምንዛሬ መጠን ሲያሰላ ዉጤቱ ብር 2,086,653.58 (ሁለት ሚሊዮን ስማንያ ሶስት ሺ ስድስት መቶ ሃምሳ ሶስት ከ58/100) የሚመጣ ሆኖ ሳለ ብር 1,959,519.45 (አንድ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሃምሳ ዘጠኝ ሺ አምስት መቶ አስራ ዘጠኝ ከ45/100) በሚል ማስቀመጡ ስህተት በመሆኑ ይህ ሊታረም ይገባል፤ ከብር 2,289,108(ሁለት ሚሊዮን ሁለት መቶ ስማንያ ዘጠኝ ሺ አንድ መቶ ስምንት) ላይ ብር 2,086,653.58 (ሁለት ሚሊዮን ስማንያ ሶስት ሺ ስድስት መቶ ሃምሳ ሶስት ከ58/100) ሲቀነስ የሚመጣዉ ብር 205,454.42 (ሁለት መቶ አምስት ሺ አራት መቶ ሃምሳ አራት ከ42/100) በመሆኑ ተጠሪ ለአመልካች የሚከፍለዉ የገንዘብ መጠን ብር 330,487.55(ሶስት መቶ ስላሳ ሽ አራት መቶ ስማንያ ስባት ከ55/100) ሳይሆን ብር 205,454.42(ሁለት መቶ አምስት ሺ አራት መቶ ሃምሳ አራት ከ42/100 ነዉ፡፡ በሌላ በኩል የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና የተያዘዉ ገንዘብ በተመለከተ የአሁን አመልካች ሰራተኛ ገንዘቡን በሰነድ ፈርመው ተቀብለዋል በማለት ቢከራከርም ፈርመው ተቀብለዋል የተባለበትን ደረሰኝ በማስረጃነት በማቅረብ መክፈሉን ያላረጋገጠ በመሆኑ እና መክፈሉን የሚያሳይ ማስረጃም በራሱ የሚገኝ ሆኖ ሳለ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሊቀርብ የሚችልበት አግባብ የሌለ በመሆኑ በዚህ ረገድ የስር ፍርድ ቤት በዋስትና የተያዘውን ገንዘብ ብር 1,844,233.00 (አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ አርባ አራት ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ ሶስት) ተጠሪ ለአመልካች እንዲመልስ ያሳለፈው ዉሳኔ የሚነቀፍ አይደለም፡፡ በመጨረሻም አመልካች ያቀረበውን የዲመሬጅ ክፍያ የዳኝነት ጥያቄ በተመለከተ የስር ፍርድ ቤት ውድቅ ያደረገው ዲሜሬጅ ለመክፈል የሚገደደው ከሳሽ እንጂ ተከሳሽ የአይደለም በሚል ነው፤ ነገር ግን የስር ከሳሽ ኃላፊ የተደረገው መርከቡ በጅቡቲ ወደብ ደርሶ ጭነት ለማራገፍ ዝግጁ በሆነበት ቀን ተሽከርካሪ በሰዓቱ ባለማቅረቡ ጭነቱ ሳይራገፍ ለቆየበት ጊዜ ሲሆን በአንፃሩ የስር ከሳሽ የዲሜሬጅ ክፍያ የጠየቀው ደግሞ ተሽከርካሪዎቹ በጅቡቲ ወደብ ደርሰው አላግባብ ቆመዋል፤ እንዲሁም ዕቃውን ወደተለያዩ መጋዘኖች ባመላለስኩበት ጊዜ ተከሳሽ መጋዘን እና ሰራተኛ ባለማዘጋጀት፣ የማራገፊያ ቦታ በመለዋወጥ የሰዓት ብክነት አስከትሎብኛል በማለት ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን በማስረጃ አጣርቶ ዉሳኔ መስጠት ሲገባዉ የዲመሬጂ ክፍያ መክፈል ያለበት ከሳሹ ነዉ በሚል ጥያቄዉን ዉድቅ ማድረጉ ስህተት በመሆኑ በዚህ ረገድ የሰጠው ውሳኔ ተሽሮ በማስረጃ አጣርቶ ሊወስን ይገባል በማለት በዚህ ነጥብ ላይ ወደ ስር ፍርድ ቤት በመመለስ ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች መጋቢት 12/2015 ዓ.ም በተፃፈ ማመልካቻ በውሳኔው ተፈጽሟል የሚለውን መሠረታዊ የሕግ ስሕተት በመዘርዘር ዲመሬጅ መኖሩን የማረጋገጥ ስራ ወይም ሃላፊነት የተሰጠዉ ለፌዴራል ትራንስፖርት ባለስልጣን ሲሆን ስልጣን የሌለዉ የተጠሪ ተወካይ የሆነዉ የኢትዮጵያ ትራንስፖርት እና ሎጂስትክ አገልግሎት ድርጂት የሰጠዉ ደብዳቤ በመሆኑ፤ እንዲሁም ተጠሪ ስለዲሜሬጂ መስረጃ ሳያቀርብና የተከፈለ ወይም የሚከፈል ድመሬጂ መኖሩ ሳይረጋገጥ አመልካች 61,794.00 የአሜሪካን ዶላር እንዲከፍል የተሰጠዉ ዉሳኔ አዋጅ ቁጥር 468/97 አንቀፅ 7(1.ሰ) የሚቃረን ነው፡፡ ዲመሬጅ እንድንከፍል የተሰጠዉ ዉሳኔም በመካከላችን የተፈፀመዉን የሚጓጓዣ ዉል አንቀፅ 4(8) እና አዋጅ ቁጥር 811/2008 አንቀፅ 8 የሚቃረን በመሆኑ ዉሳኔው ተሽሮ አመልካች ዲመሬጅ የመክፈል ኃላፊነት የለበትም ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቋል፡፡

ቅሬታው ተመርምሮ አመልካች የዲመሬጅ ክፍያ ለመክፈል የሚገደደዉ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የዲመሬጅ ክፍያ ለመደንገግ የወጣ አዋጅ ቁጥር 811/2008 አንቀፅ 8 ላይ የተመለከቱት ሁኔታዎች ሲሟሉ ነዉ በማለት የሚያቀርበዉ ክርክር ከግምት ዉስጥ ሳያስገባ ተጠሪ ዲመሬጅ ክፍያ መክፈሉ መረጋገጡን ብቻ በመጥቀስ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበዉን ክርክር ዉድቅ በማድረግ የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ግራቀኝ ባሉበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ ታዟል፡፡

ተጠሪ ህዳር 26 ቀን 2016 ዓ/ም ባቀረበው መልስ በመካከላችን ባደረግነው ውል አንቀፅ 4.8 መሠረት የአሁን አመልካች በየቀኑ ማንሳት የሚጠበቅበትን የስኳር መጠን ባለማንቱ የ 4 መርከቦች የመርከብ ዲመሬጅ USD 61,795.01(ስልሣ አንድ ሺህ ሰባት መቶ ዘጠና አምስት ከ01/100 USD) ተጠሪ በአመልካች ምክንያት የዲመሬጅ ክፍያ ለመርከብ አጓጓዥ ለኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክ አገልግሎት ድርጅት መክፈሉና በውላችን መሰረት የመዳረግ መብት ያለን ስለመሆኑ የስር ፍ/ቤት በሰነድ ማስረጃና በሰው ምስክር በማረጋገጥ አመልካች በገባው ውል መሰረት በሱ ምክንያት ተጠሪ የዲመሬጅ ክፍያ በመክፈሉ አመልካች የመክፈል ሃላፊነት አለበት ተብሎ የተሰጠዉ ዉሳኔ ህግን እና ማስረጃን መሰረት ያደረገ በመሆኑ በውሳኔው መሰረታዊ የህግ ስህተት አልፈፀመም፡፡ አመልካች ላደረሰው ጉዳት ተጠሪ ለደረሰበት የዲመሬጅ ክፍያ ከቀረው ገንዘብ ላይ ተጠሪ ቆርጦ መውሰዱ ህጋዊ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ያቀረበው አቤቱታ ውድቅ እንዲያደርግ በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም ቅሬታውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ከፍሲል ባጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን ለችሎቱ የተያዘውን ጭብጥ ከግራቀኙ ክርክርና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ ቅሬታ በቀረበበት የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ የተፈፀመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡

የአመልካች ቅሬታ እና ተጠሪው መልስ እንዲሰጥበት የተደረገው ጭብጥ ከላይ እንደተመለከተው ተጠሪ ከፈለ የተባለውን የዲመሬጅ ክፍያ አመልካች ይተካ የተባለበትን አግባብ የተመለከተ ነው፡፡ ፍሬ ነገሩን የማጣራት እና ማስረጃ መዝነው ውሳኔ የመስጠት ስልጣን በህጉ የተሰጣቸው የስር ፍርድ ቤቶች የግራቀኙን ክርክር እና ማስረጃ መርምረው ግራቀኙ ባደረጉት ዉል አመልካች የዲሜሪጅ ክፍያ የመክፈል ግዴታ እንዳለበት፤ በወቅቱ ስኳሩን ከመርከብ ላይ እንዲወርድ ባለማድረጉ የአራት መርከቦች ዲሜሬጅ እዳ 61,795.01 ዶላር መኖሩ በተገቢው ማስረጃ መረጋገጡን ወስነዋል፡፡ ይህ የፍሬ ነገርና ማስረጃ መደምደሚያ በዚህ ሰበር ችሎት ተቀባይነት ከሚያገኝ በቀር የምዝና ምክንያት ተሰጥቶ የሚለወጥበት የህግ አግባብ የለም፡፡ ስለሆነም አመልካች ግዴታውን አለመወጣቱና ስኳሩ በግዜው ከመርከብ እንዲወርድ አለማድረጉ እንዲሁም ተከፋዩ የመርከቦች ዲሜሬጅ እዳ 61,795.01 ዶላር መሆኑ በተገቢው ማስረጃ ተረጋግጦ በዚህ መልኩ ለደረሰው ኪሳራ ኃላፊነት አለበት ተብሎ በወቅቱ በነበረው ምንዛሬ ተሰልቶ አመልካች ለተጠሪ እንዲተካ መወሰኑ የሚነቀፍበት የህግ ምክንያት የለም፡፡ ውሳኔው የጭነት ማመላለሻ ተሸከርካሪዎች የዲመሬጅ ክፍያ ለመደንገግ የወጣ አዋጅ ቁጥር 811/2008 እንዲሁም ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 468/97 ድንጋጌዎችን የሚቃረን ነው የሚባልም አይደለም፡፡

ስለሆነም የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ በሕግ አግባብ ነዉ ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት ስለማይቻል የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

## ዉሳኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.219535 ታህሳስ 27 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. ግራ ቀኛቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡**

መ/ዐ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መዝገብ ቁጥር 244413

ጥቅምት 7 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች፡----- ሽመክት አሰፋ

ገበየሁ ፈለቀ

አለማየሁ ሹናራ

ተናኜ ጥላሁን

ዘዉዲቱ ታደሰ

አመልካቾች፡------ወ/ሮ አፍሪኬ ኪዳኔ -አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. ወ/ሮ ጫልቱ አሰፋ - አልቀረቡም

2ኛ. አቶ አራርሳ ኪዳኔ የሰበር አቤቱታዉ የተቋረጠ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጠ

**ፍርድ**

ለፍርዱ መነሻ የሆነው ክርክር የገጠር መሬት ይዞታን መሰረት ያደረገ በኦሮምያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በደብረ ሊባኖስ ወረዳ ፍ/ቤት የተጀመረ ሲሆን አመልካች የመቃወም አመልካች ሲሆኑ ተጠሪዎች ደግሞ የመቃወም ተጠሪዎች በመሆን በቀጥታ ክስ ክርክር ላይ 1ኛ ተጠሪ ከሳሽ ሲሆኑ 2ኛ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡አመልካች በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት የመቃወም አቤቱታ በአጭሩ፡- የክርክሩ መነሻ የሆነው 8 ቦታ የሚገኝ ይዞታ ከአባታችን አቶ ኪዳኔ ሰንበቴ እና ከእናታችን ወ/ሮ ቲኪ ደሜ የወረስኩትን 2ኛ ተጠሪ እንዲያካፍለኝ በፍ/ቤት ተወስኖ እያለ 1ኛ ተጠሪ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በነበራት የባል እና ሚስት ክርክር የጋራ ንብረት ነው በማለት ቀላቅላ አቅርባ እንድትካፈል በፍ/ቤት ያስወሰነች በመሆኑ የግል ይዞታዬ ከውሳኔው እንዲወጣልኝ ስትል ጠይቃለች፡፡

በአመልካች አቤቱታ ላይ 1ኛ ተጠሪ በሰጡት መልስም አጠር ባለ መልኩ ሲታይ የአመልካች አባት ነገሰ ማራሚ እና እናት ደግሞ  ቢፌ ኪዳኔ ሆኖ እያለ የእናት የአባታችን ይዞታ ነው በማለት ያቀረበችው ክስም ሆነ ማስረጃ ሀሰተኛ ነው፡፡ የክሱ መነሻ ሆነዉ የእርሻ መሬት የተጠሪዎች የጋራ ንብረታችን በመሆኑ አመልካች ባለቤቴን ለማገዝ ያቀረበችው ክስ  ስለሆነ የገጠር መሬት ይዞታዉ የተጠሪዎች የጋራ ሀብት ነዉ ተብሎ የተወሰነዉ በአግባቡ ስለሆነ እንዲፀናልኝ የሚል ነዉ 2ኛ ተጠሪ ደግሞ የአመልካችን ክርክር በሚደግፍ መልኩ ክርክር አቅርቧል፡፡

ግራ ቀኙን በዚህ መልኩ ያከራከረዉ የወረዳዉ ፍ/ቤቱም ይዞታው መሰረቱ የአመልካች እና 2ኛ ተጠሪ አያቶች መሆኑን በማረጋገጥ ባለፍቱ  ለ20 ዓመታት በ2ኛ ተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ እና ተጠሪዎች  ባልና ሚስቱ ለረጅም ጊዜ ሲጠቀሙበት የነበረ እና አመልካች በቦታው የማትኖር ሆና ወራሽነቷን አረጋግጣ ከመሬት ጽ/ቤት ማስረጃ ብትወስድም ከውሳኔው በፊት ተጠሪዎች ሲጠቀሙበት የነበረ መሆኑን እንጂ አመልካች ተጠቅማበት የማታውቅ ስለመሆኑ ስለተረጋገጠ መሬቱ የአመልካች አያቶች መሆኑ ቢረጋገጥም የውርስ መሬት ግን አይደለም ሲል የአመልካችን የመቋወም አቤቱታን ውድቅ በማድረግ ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በፍርዱ ቅር በመሰኘት ለሰሜን ሸዋ ከፍተኛ ፍ/ቤት  ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ቅሬታ  ቢያቀርቡም  ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በማፅናት  ወስኗል፡፡

አመልካች በውሳኔው ቅር ተሰኝተው ለኦሮምያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም በፍ/ብ/ስ/ስ ሕግ ቁጥር 337 መሰረት አያስቀርብም በሚል ዉሳኔ አስተላላፏል፡፡

በመቀጠል አመልካች ቅር ተሰኝተው የሰበር  አቤቱታ ለኦሮምያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

ይህ ሰበር አቤቱታ የቀረበው አመልካች የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ እንዲታረም በማለት ሲሆን የቀረበው የሰበር አቤቱታም አከራካሪው መሬት ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በፍ/ቤት ተከራክረን አሸንፌ በአፈጻጸም አልቆ የባለይዞታነት ማስረጃ ተሰጥቶኝ እያለ የተሰጠው ውሳኔ ባልተሻረበት ወይንም ከመፈጸሙ በፊት ባልተቃወሙበት ሁኔታ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ከፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 5 አንጻር ስህተት በመሆኑ እና የፍ/ቤት ውሳኔ የለም ቢባል እንኳን ይዞታው የአባቴ እና እናቴ ስለመሆኑ በማስረጃ ስለተረጋገጠ የመውረስ መብት የሚያሳጣ ውሳኔ ሊሰጥብኝ አይገባም በገጠር መሬቱ ማስረጃ ከተሰጠኝ በኂላ መጠቀም ስለጀመርኩኝ  በፍ/ብ/ህ/ቁ 1195 መሰረት ባለይዞታ ሆኜ የመቆጠር መብት እያለኝ ስለሆነ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲታረም ሲሉ ጠይቋል፡፡

አመልካች ያቀረቡትን የሰበር ቅሬታ መነሻ ተደርጎ ምንም እንኳን 1ኛ ተጠሪ በክርክሩ ተካፋይ ባይሆኑም አመልካች በ2ኛ ተጠሪ ላይ ክስ መስርተው በመዝገብ ቁጥር 24330 ክርክር ያስነሱ ይዞታዎች ለአመልካች ተወስኖላቸው በአፈጻጸም እንደተረከቡ በተገለጸበት እና ቢያንስ 2ኛ ተጠሪ በአመልካች የቀረበባቸውን ክስ አምነው የተወሰነላቸው እንደመሆኑ መጠን የባል እና ሚስት ይዞታ ክፍፍል ሲደረግ ለ2ኛ ተጠሪ የደረሰባቸው ድርሻ ውስጥ አመልካች ያስወሰኑት ይዞታዎች

ተለይተው ለአመልካች እንዲቀየሩ በስር ፍ/ቤት ያልተወሰነበትን አግባብነት ለማጣራት ሲባል ተጠሪ መልሳቸውን እንዲያቀርቡ ተብሏል ።

1ኛ ተጠሪ ባቀረቡት መልስም አመልካች በእኔ ላይ ክስ መስርታ ያስወሰነችው ነገር የክሱ መነሻ በሆነዉት መሬቶች ላይ አመልካች በ2ኛ ተጠሪ ላይ ክስ መስርቼ በመዝገብ ቁጥር 24330 ላይ አስወስኛለቸዉ ባለችዉ ላይ 1ኛ ተጠሪ ተካፋይ ያልሆነኩበትና የሀሰት ማስረጃ በመሆኑ መሬቱን 20 ዓመት በላይ በባል እና ሚስት (ተጠሪዎች) ይዘን ስንጠቀም የቆየን መሆኑ ተረጋግጦ እኩል እንድንካፈል የተወሰነልን በመሆኑ ከዚህ አኳያ የስር ስር ፍርድ ዉሳኔ ይፅናልን ሲሉ መልስ ሰጥቷል።

2ኛ ተጠሪን በተመለከተ ይህ ፍርድ ቤት በቀን 11/11/2016 ዓ.ም በተሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረት አመልካች 2ኛ ተጠሪ ላይ ያቀረበችዉን የሰበር ቅሬታ በተመለከተ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 70 (መ) መሰረት 2ኛ ተጠሪን ከክርክሩ ዉጪ አድርጎቷል።

ይህ ፍርድ ቤትም ያስቀርባል የተባለበትን ጭብጥ መሰረት በማድረግ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ላይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈፅማል ወይስ አልተፈፀመም ? የሚለዉን ከሕጉ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ ተመርምሯል።

እኛም መዝገቡን እንደመረመርነዉ የአሁን አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረበቸዉ የመቋወም አመልካች አቤቱታ ላይ በፍርድ ቤት ዉሳኔ ያገኘሁትን መሬቶች ተጠሪዎች በባልና ሚስት ክርክር በፍርድ ቤት ዉሳኔ እንዲያገኝ አድርገዉ የአመልካችን መሬት ቀላቅለዉ ያስወሰኑ በመሆኑ የተቀላቀለዉ መሬቴ ይዉጣልኝ የሚል ሲሆን 1ኛ ተጠሪ በበኩላ የአመልካች መሬት ተጠሪዎች ተከራክረን ባስወስነዉ የባልና ሚስት መሬት ጋር አልተቀላቀለም አመልካች የጠቀሰቸዉ የፍርድ ቤት ዉሳኔ ላይ 1ኛ ተጠሪ ተካፋይ ያልሆኑኩበት ነዉ አሁን አመልካች እየጠቀሰች ያለዉ መሬት ተጠሪዎች ባልና ሚስት በመሆን መሬቱን ከ20 አመታት በላይ እየተጠቀምንበት ያለና የይዞታ ማረጋገጫዉም በባለቤቱ 2ኛ ተጠሪ ስም የሚታወቅ ስለሆነ የአመልካች ክርክር 2ኛ ተጠሪን ለማገዝ የቀረበ ስለሆነ ተገቢነት የለዉም የሚል ክርክር አቅርባ የስር ፍርድ ቤትም የክርክሩ መነሻ የሆነዉን የገጠር እርሻ መሬት በተመለከተ አመልካች በመሬቱ ተጠቅማ ስለማታዉቅ የፍርድ ቤት ዉሳኔ ቢኖራትም መሬቱ አይገባትም ሲል ድምዳሜ ላይ ደርሷል።

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች በፍርድ ቤት ያገኙት የገጠር መሬት ተጠሪዎች የባልና ሚስት ክርክር ሲያደርጉ ቀላቅለዉ ያስወሰኑ በመሆኑ ይለይልኝ የሚል ዳኝነት ሲሆን አመልካች በጠየቀችዉ ዳኝነት መሰረት ተደርጎ 1ኛ ተጠሪም የአመልካችን መሬት አልየዘኩም የሚለዉ በተመለከት አመልካች ፍርድ ያገኘቸዉ መሬት ተጠሪዎች ባልና ሚስት ክርክር አድርገዉ ባስወሰኑት መሬቶች ዉስጥ ተቀላቅላል ወይስ አልተቀላቀለም ? በሚለዉ ላይ ተገቢዉን ጭብጥ ሳይመሰርት እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት በርግጥም የአመልካችን በፍርድ ቤት ዉሳኔ ያገኘችበትን መሬትን 1ኛ ተጠሪ ያለአግባብ የባልና ሚስት ክርክር የንብረት ዝርዝር ዉስጥ አስገብታ የአመልካችን መሬት ምን ያህሉ ተቀላቅሎ ዉሳኔ አርፎበታል የሚለዉ የዳኝነት ጥያቄ በአግባቡ ሳይጣራ በግልፅ የተጠየቀዉን የዳኝነት ጥያቄ ይህም በፍርድ ቤት ዉሳኔ ያገኙት መሬት ያለአግባብ ተጠሪዎች

ባልና ሚስት ክርክር ዉስጥ ቀላቅለዉ አስወስኖብኛል የሚለዉ ጥያቄ ወደ ጎን በመተዉ አመልካች በመሬቱ ተጠቅማ አታዉቅም በሚል አመልካች በጠየቀቻቸዉ የዳኝነት ጥያቄ ላይ ግልፅ የሆነ ዉሳኔ ሳይሰጥ የታለፈ ሲሆን በተጠየቀ ዳኝነት ላይ ግልፅ የሆነ ፍርድ ያለመስጠት መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለመሆኑ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 39144 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም የተሰጠበት በመሆኑ አሁን በእጃችን ባለዉ ጉዳይ አመልካች በፍርድ ቤት ዉሳኔ ያገኘሁት መሬት ተጠሪዎች የባልና ሚስት ክርክር አድርገዉ በተሰጠዉ ዉሳኔ ዉስጥ መሬቴ ተቀላቅሎ ዉሳኔ ያረፈበት ስለሆነ መሬቶቹ ይለይልኝ የሚለዉን ጉዳይ የአመልካች በፍርድ ያገኘቻቸዉ ገጠር መሬት ተጠሪዎች ባልና ሚስት ሆነዉ ተከራክርዉ ባስወሰኑት ዉሳኔ ዉስጥ ተቀላቅላል ወይስ አልተቀላቀለም የሚለዉ ጭብጥ ላይ ግልፅ የሆነ ዉሳኔ ሳይሰጥበት ታልፎ አመልካች መሬቱን ተጠቅማ ስለማታዉቅ የገጠር መሬት ላይ ባለመብት ልትሆን አይገባም ሲሉ የተሰጠዉ ዉሳኔ አግባብነት የሌለዉ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡በመሆኑም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቶበታል፡፡

**ዉሳኔ**

1/ የደብረ ሊባኖስ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 27143 ላይ በቀን 10/2/2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ፣የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 90671 ላይ በቀን 5/3/2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የኦሮ/ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 411074 ላይ በቀን 30/3/2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት እና የኦሮ/ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 420878 ላይ በቀን 21/6/2015 ዓ.ም የተሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በፌ/ጠ/ፍ/ቤት የሰበር ስነ- ስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9(1)(ለ) መሰረት ተሽሯል፡፡

2/ የደብረ ሊባኖስ ወረዳ ፍርድ ቤት የተዘጋዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ አመልካች በፍርድ ቤት ዉሳኔ ያስጠችበት የገጠር እርሻ መሬቶች 1ኛ ተጠሪ ባልና ሚስት ንብረት በማለት ባቀረበቸዉ ክስ ዉስጥ ተቀላቅሎ ዉሳኔ ያረፈበት መሆኑንና ያለመሆኑን ከሚመለከተዉ የወረዳዉ መሬት

አስተዳዳር ጽ/ቤት መግለጫ እንዲቀርብለት በማድርግ ፣ የመዝገብ ቁጥር 24330 በትዕዛዝ ዉሳኔ ከሰጠበት ፍርድ ቤት መዝገቡን በትዕዛዝ በማስቀረብ በዉሳኔ ዉስጥ የተጠቀሱት የመሬቶቹ አዋሳኞች 1ኛ ተጠሪ በባልና ሚስት ክርክር ዉስጥ የጠቀሰቻቸዉ እና ዉሳኔ ካረፈባቸዉ መሬቶች ጋር ተመሳሳይ መሆናቸዉና አለመሆናቸዉን በመለየት እና በመርመር በሕጉ መሰረት እንዲወስን በፌ/ጠ/ፍ/ቤት የሰበር ስነ- ስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9(2) መሰረት ወደ ስር ፍርድ ቤት ተመልሷል፡፡

3/ አመልካችና የስር 2ኛ የመቋወም ተጠሪ በመዝገብ ቁጥር 24330 ላይ የገጠር እርሻ መሬት ዉርስ ይገባናል በሚል ተከራክረዉ ባስወሰኑት ዉሳኔ ላይ የአሁን 1ኛ ተጠሪ ዉሳኔዉን ለመቋወም ይህ ፍርድ አያግዳትም ተብሏል፡፡

4/ ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ወገኖች ይቻቻሉ፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ዉሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁጥር 244435

ጥቅምት 06 ቀን 2017 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው
በዕውቀት በላይ
ቀነዓ ቂጣታ
ብርሃኑ መንግስቱ
ማርታ ተካ

አመልካች፡- ወ/ሮ ነጠር መርሻ
ተጠሪ፡- ወ/ሮ ካሳነሽ በለጠ
መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች መጋቢት 05 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በፋርጣ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 21628 በቀን 10/02/2015 ዓ.ም ክርክር ያስነሳው መሬት የተጠሪ እናት በምሪት ያገኙት ስለሆነ አመልካች ሊለቁ ይገባል በሚል መወሰኑና በየደረጃው ያሉት ፍርድ ቤቶችም ይህንኑ ውሳኔ በትእዛዝ ማጽናታቸው መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የገጠር መሬትን በሚመለከት የቀረበን ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፋርጣ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካች ተከሳሽ፤ የአሁን ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ የአሁኗ ተጠሪ ክስ ይዘት፡- በፋርጣ ወረዳ የሚገኝ አዋሳኙ በክስ አቤቱታው ላይ የተገለጸ መሬት ለተጠሪ እናት በምሪት የተሰጠ ሆኖ እያለ አመልካች ምንም ዓይነት መብት ሳይኖራቸው መሬቱን የያዙ መሆኑን በመግለጽ አመልካች መሬቱን ለቀው እንዲያስረክቧቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

አመልካች በሰጡት መልስ የተጠሪ ክስ የአዋሳኝ ስህተት ያለበትና ግልፀኝነት የጎደለው መሆኑን፤ አመልካች መሬቱን ከ1983 ጀምሮ ይዤ የምጠቀምበት በመሆኑ የተጠሪ ክስ በይርጋ ቀሪ ሊሆን ይገባል የሚሉ መቃወሚያዎች በማስቀደም በፍሬጉዳይ ላይ በሰጡት መልስ ክርክር የተነሳበት መሬት አመልካች በ1983ዓ.ም ከባለቤቴ ከአቶ መኮንን አካሉ ጋር በጋራ በባልና ሚስት በህጋዊ መንገድ ተመርተን በመሬቱ ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ተሰጥቶን ይዘን የምንጠቀምበት መሬት ስለሆነ ልለቅ አይገባም በሚል መልስ ሰጥቷል፡፡

የወረዳ ፍርድ ቤቱም በመቃወሚያው ላይ ግራቀኙን አከራክሮ የተጠሪ ክስ በይርጋ ቀሪ በማድረግ ብይን ሰጥቶ የነበረ ቢሆንም ተጠሪ ለክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱ በመ/ቁ 78299 ግራቀኙን አከራክሮ የተጠሪ ክስ በይርጋ ቀሪ አይሆንም በማለት የስር ውሳኔ በመሻር በፍሬጉዳይ ላይ አከራክሮ እንዲወስን መልሶታል፤ የወረዳው ፍርድ ቤት በፍሬጉዳይ ላይ ግራቀኙን አከራክሮ ምስክሮችን ከሰማና ከመሬት አስተዳደሩ ተገቢውን ማስረጃ እንዲቀርብለት አድርጎ ፍሬ ነገሩን ከአጣራ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ምንም እንኳ ክርክር ያስነሳው የእርሻ መሬት ከ1983ዓ.ም ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ እየተጠቀሙበት የሚገኙት አመልካች መሆናቸው በግራቀኙ በኩል ቀርበው በተሰሙት ምስክሮች ቢረጋገጥም መሬቱን ከመነሻው ለተጠሪ እናት የተመሩት በመሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ በክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 17 መሰረት ተጠሪ የሟች እናታቸው መሬት የመውረስ መብት ስላላቸው አመልካች መሬቱን ለተጠሪ ሊለቁ ይገባል በሚል በመ/ቁ 21628፤ በቀን 10/2/2015ዓ.ም ወስኗል፡፡

አመልካች በውሳኔው ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም በመ/ቁ 84225 በቀን 23/03/2015 ዓ.ም ይግባኙን ባለመቀበል በፍ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

በመቀጠል አመልካች ለክልሉ ሰበር ችሎት ያቀረቡት አቤቱታም የስር ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አላገኘሁበትም በማለት በመ/ቁ 03-119655 በቀን 01/06/2015 ዓ.ም አቤቱታቸውን ውድቅ በማድረግ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በቀን 05/07/2015ዓ.ም የተፃፈ ሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን የሰበር አቤቱታቸው ይዘትም ሲታይ፡- ተጠሪ በክሳቸው አዋሳኝ የጠቀስኩት መሬት አመልካች ባልያዝኩበት ክሳቸው ግልጽነት የጎደለው ነው በሚል ያነሳሁት ክርክር ውድቅ መደረጉ ተገቢ አለመሆኑ፤ ክርክር ያስነሳው መሬት

ከ1983ዓ.ም ጀምሮ ከ30 ዓመት በላይ ይዤ መጠቀሜ በስር ፍርድ ቤት ተረጋግጦ እያለ የተጠሪ ክስ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1845 እና በአማራ ክልል አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀፅ 55 መሰረት መብታቸው በይርጋ ቀሪ መሆን ሲገባው ይርጋ አይታገድም መባሉ ተገቢ፤ የተጠሪ እናት በመሬቱ ባለመብት ባልሆነችበት የተጠሪ ወራሽ የሆኑት አመልካች ይህኑ መሬት ሊወርሱ የሚችሉበት የህግ አግባብ የለም፤ ፋርጣ ወ/መ/አስ/አከባቢ ጥበቃ በቀን 04-02-2014 ዓ.ም ጽፎ ለስር ፍርድ ቤት በሰጠው ምላሽ የሚያስረደው አከራካሪው መሬት ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ በአመልካች እጅ የቆየ እና እስካሁን ያለ መሆኑን የሚስረዳ ሆኖ እያለ፤ ተጠሪ ደብተር ሳይኖራቸውና እናታቸውም ይህንኑ መሬት ከ1983ዓ.ም ጀምሮ ይዘው የማያውቁትን ለረዥም አመታት መሬቱ በእጄ የቆየ እና የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ተሰጥቶኝ የያዝኩት መሬት ሆኖ እያለ መሬቱን ለቅቄ ለተጠሪ እንዳስረክብ መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ እንዲታረምልኝ የሚል ነው፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም አቤቱታውን በመመርመር፡- የአመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ የሆነ ነው በማለት ያቀረቡት መከራከሪያ ውድቅ የተደረገው በአግባቡ ነው ወይ? የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ መደረጉ ተገቢ ነው የሚባል ከሆነ አከራካሪው መሬት ከ1983 ዓ.ም ለተጠሪ እናት ተደልድሎ የነበረ መሆኑ የተረጋገጠ ቢሆንም ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ የተጠሪ እናት ይዘው ባለመጠቀማቸው መሬቱን አመልካች ከባለቤታቸው ጋር ይዘው እየተጠየቀሙ እንደቆዩ እና በስማቸው ተመዝግቦ እንደሚገኝ እንዲሁም የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር እንዳላቸው በተረጋገጠበት ይዞታውን ለቀው ለተጠሪ እንዲስረክቡ የመወሰኑን አግባብነት ከአዋጅ ቁጥር 252 /2009 አንቀፅ 2(21 እና 25)፣ 8/1፣9፣14 እና 35(2 እና5) እንዲሁም ከኢፌዲ.ሪ ህግ መንግስት አንቀፅ 40/4 ስር ከተደነገገው አንፃር ተገቢ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር በሚል ተጠሪ በጉዳዩ ላይ መልሳቸውን እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በቀን 02/07/2017 ዓ.ም ጽፈው የሰጡት መልስ ይዘቱም፡- የተጻፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ በክልሉ አዋጅ ቁጥር 252 /2009 መሰረት አንቀፅ 11 ላይ መሬት ሊገኝ የሚችለው በድልድል በወርስ እና በስጦታ ብቻ ነው፡፡ በዚሁ አዋጅ አንቀፅ 55 የገጠር መሬትን በወረራ ወይም በሌላ በማንኛውም አካል በህገ ወጥ መንገድ ይዞ የሚገኘውን እንዲለቅ ሲጠየቅ የይርጋ መቃመወያ ሊነሳ አይገባም፡፡ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 40/4 ማንኛውም ሰው መሬቱን በማንኛውም መንገድ ሊነጠቅ እንደይማይችል የሚስቀምጥ ሲሆን ከዚህ ጋር በተያያዘ የሰ/መ/ቁ 179827 ቅፅ 24 ላይ ተመሳሳይ ውሳኔ መስጠቱን፤ በስር ፍርድ ቤት መሬቱን በወቅቱ መጠየቅ ያልተቻለው የተጠሪ እናት አቅመ ደካማ ስለነበሩ እና አመልካች በማን አለብኝነት እና በጉልበት መሬቱን መያዛቸው በሰው ምስክር አረጋግጠናል፤ አመልካች በተጠሪ እናት መሬት ላይ ያለአግባብ ደብተር የተሰጣቸው ቢሆንም በአዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀፅ 35/2/5 መሰረት ደብተር ካለው ይህንን የሚቃረን ማስረጃ በማቅረብ ማስተባበል የሚቻል በመሆኑ መሬቱ የተጠሪ እናት ከሌሎች ሰዎች ጋር ሆነ የተመራችው መሆኑን በምስክሮችም ሆነ በወረዳው መሬት አጠቃቀም በሰጠው ምላሽ ተረጋግጧል፡፡ በዚህ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

መሰረት የቀረበው ማስረጃ ደብተሩን ሊያስተባብል የሚችል በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት አደለም ተብሎ እንዲፀናላቸው በመጠየቅ መልስ ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፣ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡ በዚህ ጉዳይ እልባት ማግኘት የሚገባቸው ጭብጦች የአመልካች የይርጋ መቃወሚያ በስር ፍርድ ቤቶች ውድቅ ተደርጎ ለክርክሩ መነሻ የሆነው የእርሻ መሬት አመልካች ለቀው ለተጠሪ እንዲያስረክቡ መወሰናቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽመዋል ሊባል የሚችል መሆን አለመሆኑ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

እንደመረመርነውም የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ በ1983ዓ.ም እናቴ በምሪት ያገኘችውን በክሱ አዋሳኙ የተጠቀሰው መሬት አመልካች ከህግ አግባብ ውጪ በሆነ መንገድ ስለያዙብኝ ለቀው ያስረክቡን የሚል ሲሆን በአመልካች በኩል ክርክር ያስነሳው መሬት ከ1983ዓ.ም ጀምሮ የያዝኩትና የይዞታ ማረጋገጫ ደብተርም ያለኝ በመሆኑ ከ30 አመት በኃላ በተጠሪ በኩል የቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ሊሆን ይገባል በሚል በመልሳቸው በመቃወሚያነት በማንሳት ተከራክረዋል፡፡ በስር ወረዳው ፍርድ ቤት የተጠሪ ክስ በይርጋ ቀሪ በማድረግ ብይን ሰጥቶ የነበረ ቢሆንም በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱ የይርጋ መቃወሚያው ውድቅ ተደርጎ በፍሬጉዳይ ላይ አከራክሮ እንዲወስን መመለሱን ከስር ውሳኔ ግልባጭ ለመረዳት ተችሏል፡፡

በስር ፍርድ ቤቶች ክርክር ያስነሳው መሬት በ1983 ዓ.ም ለተጠሪ እናት በምሪት ከተሰጠ በኃላ የተጠሪ እናት በመሬቱን ባለመጠቀማቸው አመልካች ከባለቤታቸው ጋር ከ1983ዓ.ም ጀምሮ ይዘው የሚጠቀሙበትና በስማቸው የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ያላቸው መሆኑን ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍ/ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም በስር ፍ/ቤት ከተረጋገጠው ፍሬነገር አንጻር በየደረጃው ያሉ ፍ/ቤቶች ይርጋን በተመለከተ የሰጡት ውሳኔ አግባብነት ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 55 ድንጋጌ አንጻር ስንመለከት የክልሉ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተጠሪን ክስ በይርጋ አይታገድም ከሚል መደምደሚያ ላይ ሊደርስ የቻለው አመልካች አከራካውን መሬት በሕጋዊ መንገድ የያዙት ስለመሆኑ እስካልተረጋገጠ ጊዜ ድረስ መሬቱን የያዙት በሕገወጥ መንገድ መሆኑ ግምት የሚወሰድበት በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 55 እና 2/39 መሠረት የይርጋ መቃወሚያን በስነ-ስርዓት መቃወሚያነት ሊያነሱ አይችሉም በሚል ነው፡፡

ይህ የስር ፍርድ ቤት መደምደሚያ ከተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 252 /2009 ድንጋጎች አንፃር መመርምሩ አስፈላጊ ነው፡፡ የአዋጁ አንቀፅ 2(39) ድንጋጌ መሰረት ሕገ-ወጥ ይዞታ ማለት ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ የተያዘና አግባብ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ባለው አካል እውቅና ያልተሰጠው ማናቸውም የገጠር መሬት ይዞታ መሆኑን ትርጉም ሰጧል፡፡ በዚህ ድንጋጌ አመልካች ይዞታውን የያዙት በህገወጥ መንገድ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ነጥብ ሲመዘን አመልካች በስር ፍርድ ቤቶች ክርክር ያስነሳው መሬት በ1983 ዓ.ም ለተጠሪ እናት በምሪት ከተሰጠ በኃላ የተጠሪ እናት በመሬቱ ባለመጠቀማቸው ከ1983ዓ.ም ጀምሮ አመልካች መሬቱን ይዘው የሚጠቀሙበትና በስማቸው የይዞታ ማረጋገጫ የተሰጣቸው መሆኑ አዋጁ በሰጠው ትርጉም መሰረት ሕገወጥ ነው የሚያስብል አይደለም፡፡

በሌላ በኩል አመልካች መሬቱን የያዙት በክልሉ የገጠር መሬት ሕግ መሠረት በሚመለከተው የአስተዳደር አካል ተፈቅዶላቸው በሕጋዊ መንገድ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ተሰጥቶኣቸው ከ30 አመት በላይ ይዘው የሚጠቀሙበት መሬት መሆኑና በህገወጥ መንገድ እንዳልያዙ እስከተረጋገጠ ድረስ የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ ከሟች እናቴ በውርስ የሚገባኝን መሬት አመልካች ስለያዘች ለቃ ታስረክበኝ የሚል በመሆኑ የእርሻ መሬት ይዞታና ተጠቃሚነት መብት ለማረጋገጥ የሚቀርብ ክስ የይርጋ የጊዜ ገደብ ሊኖረው የሚገባው ሲሆን የይርጋ የጊዜ ገደብም አርሶ አደሩ ከህጋዊ ይዞታ መሬቱ ያለመፈናቀል መብት ያለው ስለመሆኑ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 40/4/ የተረጋገጠውን መብት የሚያሳጣ በመሆኑ የእርሻ መሬቱ ባለይዞታና ተጠቃሚ ነኝ የሚለው ሰው መብቱን ለማስከበር የተሻለና ሰፊ ጊዜ የሚሰጠው በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1677/1/ እና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1845 የተደነገገው የአስር ዓመት የይርጋ የጊዜ ገደብ ተፈፃሚነት ያለው መሆኑን ይኸው ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 69302 እና በሌሎች መዝገቦች አስገጃጅ ትርጉም የሰጠበት በመሆኑ የተጠሪ ክስ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1677(1) እና 1845 መሠረት በ10 ዓመት ይርጋ የማይታገድበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም በስር ፍርድ ቤቶች አመልካች መሬቱን በህገወጥ መንገድ እንደያዙት ተደርጎ የተጠሪ ክስ በይርጋ የሚታገድ አደለም በሚል መወሰናቸው ሊታረም የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል በዚሁ መሰረት ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. የፋርጣ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 21628 በቀን 10/02/2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣ የደ/ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 84225 በቀን 23/03/2015 ዓ.ም የሰጠው ብይን፣ እንዲሁም የአማራ ክልል ብሄራዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 119655 የሰጠው ትዕዛዝ የሰበር ስነ- ስርኣት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1/ለ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የተጠሪ ክስ በ10 አመት ይርጋ ቀሪ በመሆኑ አመልካች አከራካሪው የመሬት ይዞታ ለቀው ለተጠሪ ሊያስረክቡ አይገባም በሚል ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት ምክንያት የወጣውን ወጭና ክሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

መ/ዐ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የሰበር መ/ቁ 244497

ጥቅምት 08 ቀን 2017 ዓ/ም

ዳኞች - ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻዉ አዳነ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሰናይት አድነዉ

ሀፊዝ አባጀማል

አመልካች ፡- ወ/ሮ ንግስት ብርሃኔ

ተጠሪ ፡- አቶ ዘለቀ ብርሃኔ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከለታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ የፍርድ አፈፃፀምን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረዉ በአማራ ክልል ደብረማርቆስ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የአሁን አመልካች የአፈ/ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ የአፈ/ተከሳሽ ተብለው ተሰይመዋል፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው የአሁን አመልካች ባቀረቡት የአፈፃፀም አቤቱታ ከተጠሪ ጋር በነበረዉ ክርክር በመዝገብ ቁጥር 16968 የካቲት 01 ቀን 2013 ዓ/ም አመልካች ለተጠሪ ያደረጉት ስጦታ ዉል ፈራሽ ነዉ ተብሎ ተጠሪ የአመልችን የእርሻ መሬት ለቆ እንዲያስረክብ፤ በስጦታ ውሉ መሰረት ተጠሪ በተሰጠው መሬት ላይ የሰራዉ ቤት ከእነ መዉጫ እና መግቢያዉ ተጠሪ ሊለቅ አይገባም ተብሎ የተወሰነ ሲሆን ይኸው ዉሳኔ በምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ

ቤት እና የኢ.ብ.ክ.መ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የፀና በመሆኑ በዉሳኔው መሰረት ይፈፀምልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

የአፈፃፀም አቤቱታው የቀረበለት የስር ፍርድ ቤት እንደ ውሳኔው ለማስፈጸም ከደ/ማ/ከ/አካ/ጥ/መ/አስ/ፅ/ቤት ባለሙያ በተገኘበት ጉዳዩን ከቦታዉ ድርስ ሄዶ በማጣራት የአሁን ተጠሪ የሰሩት ቤት በቁመት 10 ሜትር በወርድ ደግሞ በሜትር 5.30 ሜትር መሆኑን፤ የቤቱ መዉጫና መግቢያ በሰሜን አቅጣጫ በመሆኑ በዚህ አቅጣጫ የአካባቢዉ ማህበረሰብ ወደ ቤተክርስትያን የሚሄዱበት መንገድ መሆኑን አረጋግጦ በቤቱ ፊት ለፊት ለሽንት ቤት፣ ለማድቤት፣ ለከብት ቤት እና ለከብት መኖ መከመርያ ቦታ ታሳቢ በማድረግ መዉጫና መግቢያ የሚሆን ቦታ ወርዱ 11.5 በቁመት ደግሞ 29.5 ሜትር ለአሁን ተጠሪ በማስረከብ ቀሪ ክርክር የተነሳትን የእርሻ መሬት ለአሁን አመልካች አስረክብናል በማለት የአፈፃፀም መዝገቡን ዘግቷል፡፡

አመልካች በዚህ የአፈፃፀም ውሳኔ ቅር ተሰኝተዉ ለምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱ በቀረበለት ይግባኝ አቤቱታ ላይ የግራቀኝ ክርክር ከሰማና ከምስራቅ ጎጃም ዞን አካ/ጥ/መ/አስ/መምሪያ የተሰጠውን ተጨማሪ ማብራሪያ ከመረመረ በኃላ የስር ፍርድ ቤት አፈፃፀም ችሎት ከቦታዉ ድርስ በመሄድና በባለሙያ በማጣራት ተጠሪ በግብርና ስራ የሚተዳደሩ መሆኑን፤ ለሰዉ መዉጫ መግቢያ፣ ለሽንት ቤት፣ ለማድቤት፣ ለከብት ቤት እና ለከብት መኖ መከመርያ ቦታ የሚያስፈልግ መሆኑን አረጋግጦ እንዲሁም መዉጫ እና መግቢያውን ቦታ ተጠሪ ከዚህ በፊት የሚጠቀሙበት ቦታ እንጂ ተጨማሪ ቦታ እንዳልተሰጠ አረጋጦ የወሰነ በመሆኑ፤ እንዲሁም በዞኑ አካ/ጥ/መ/አስ/መምሪያ እንደተገለፀው መዉጫ መግቢያ ከ 3 እስከ 4 ሜትር ስፋት ብቻ እንዲያገኝ ቢደረግ የተጠሪን የአኗኗር ሁኔታ የሚያከብድ እና በግራቀኝ መካከል ያለዉን ማህበራዊ ኑሮ ለፀብ እና ጭቅጭቅ የሚጋብዝ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት የወሰነዉ የመዉጫ መግቢያ የቦታ መጠን በዝቷል ሊባል የሚችል አይደለም በማለት በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረቡትን ቅሬታ ውድቅ በማድረግ ዉሳኔውን አጽንቷል፡፡

አመልካች በመጨረሻ ለአ/ብ/ክ/መ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም ተብሎ አቤቱታቸው ውድቅ ተደርጓል፡፡

የሰበር አቤቱታው ለዚህ ፍርድ ቤት ቀረበው በዚህ ነው፡፡ አመልካች ባቀረቡት ማመልከቻ ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉ ቦታ ግራቀኝ ባለንብት እና ባለሙያ በተገኘበት ሲለካ ቤቱ በወርድ 10

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ሜትር በቁመት 5.30 ሜትር በመሆኑ ስፋቱ በ 53 ካ/ሜትር ቦታ ላይ ያረፈ ቤት ተጠሪ ሲረከብ ቅሬታ ያላቀረቡኩ ሲሆን ለመዉጫ መግቢያ በሚል የተሰጠው ይዞታ ግን ከህግ እና ከመመርያ ዉጭ ነው፡፡ የዞኑ ባለሙያ ከቦታዉ ድረስ በመሄድ የአካባቢዉ ማህበረሰብ ለመዉጫ መግቢያ የሚጠቀመዉ ከ 3 እስከ 4 ሜትር ያላነሰ ቦታ ነዉ በማለት አረጋግጦ እያለ ከዚህ በላይ አለአግባብ ለተጠሪ እንዳስረክብ የተሰጠዉ ዉሳኔ ከዉሳኔዉ መንፈስ እና አላማ ዉጭ የሆነ እና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታም ይገባል፡፡ ተጠሪ ነጋዴ ሲሆን የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ አርሶ አደር መሆኑን ሳያጣራ ግምት በመዉሰድ እና ከ 3 እስከ 4 ሜትር ቦታ ለአርሶ አድር ለተለያዩ ግልጋሎቶች በቂ አይደለም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ የአመልካችን መብት እና ጥቅም የሚጎዳ በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታቸዉን አቅርበዋል፡፡

ቅሬታው ተመርምሮ ፍርድ የሚፈፀመዉ እንደ ፍርዱ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 378 እና ተከታይ ድንጋጌዎች የተመለከተ እንዲሁም የፍርድ አፈፃጸም መሰረታዊ መርህ ከመሆኑ አንፃር ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ መዉጫ መንገድ በተመለከተ ከሚመለከተዉ ገጠር መሬት አስተዳደር የቀረበዉን መግጫ ግምት ዉስጥ ሳይገባ መዉጫ መንገድ 11.5 ሜትር በ29.5 ሜትር እንዲሆን የተሰጠው ዉሳኔ እንዲፈፀም ቀረበዉን ፍርድ የተከተለ መሆን አለመሆኑን አጣርቶ ለመወሰን በሚል ጉዳዩ ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በሰጡት መልስ ለአፈፃፀም ምክንያት የሆነው በደ/ማርቆስ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 16968 የተሰጠዉ ዉሳኔ የሥጦታ ዉሉ ፈርሶ የአሁን ተጠሪ በስጦታ የተረከብኩትን መሬት ለአሁን አመልካች እንዳስረክብ፤ ከዚሁ መሬት ላይ ተጠሪ በአመልካች እዉቅና እና ፈቃድ የሰራሁት ቤት ሳይፈርስ ለመዉጫ እና መግቢያ መንገድነት የምጠቀምበትን መሬት ጨምሮ ላስረክብ እንደማይገባ ዉሳኔ የተሰጠ በመሆኑ አፈጻጸም ችሎቱ የወረዳዉን መሬት አጠቃቀም ባለሙያ ይዞ ከቦታዉ ድረስ ችሎቱ በአካል ወርዶ ቤት የሰራሁበትን ቦታ እና በመዉጫ መግቢያ መንገድነት እየተጠቀምኩበት ያለዉን ቦታ በልኬታ በማረጋገጥ 11.5 ሜትር በወርድ እንዲሁም ከመኖሪያ ቤቱ እስከ መንገዱ ድረስ 29.5 ሜትር በቁመት ያለዉን ቦታ ለክቶ በማስቀረት ለአሁን የሰበር አመልካች ቀሪዉን ቦታ አስረክቧል፡፡ ከዚህ አንጻር የስር ወረዳ ፍ/ቤት የአፈጻጸም ችሎትም ሆነ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ የሚነቀፍ አይደለም፡፡ የምስ/ጎ/ዞ/ከ/ፍ/ቤት ከምስራቅ ጎጃም ዞን አካ/ጥ/መ/አስ/መምሪያ ማብራሪያ ሲጠይቅ ለመዉጫ መግቢያ መንገድ ከ3 እስከ 4 ሜትር በቂ ነዉ በማለት የገለፀው በመመሪያ የተደገፈ ሳይሆን የራሳቸዉን ግምታዊ አስተያየት የሰጡበት በመሆኑ እና የመሬት አጠቃቀም ባለሙያዉ በችሎት ቀርበዉ በማጣሪያ ምስክርነት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ቃላቸዉን የሰጡ ሲሆን በሰጡት ቃልም የአሁን የሰበር ተጠሪ በመዉጫ መግቢያ መንገድነት ሲጠቀሙበት ከነበረዉ መሬት ዉጭ ሌላ አዲስ መሬት ከሰበር አመልካች ይዞታ ላይ ተቀንሶ ለመንገድነት ያልተሰጠ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ይህም የሚያሳየዉ የአፈጻጸም ችሎቱ በዋናዉ መዝገብ በተሰጠዉ ዉሳኔ መሰረት ለመዉጫ መግቢያ መንገድነት በአሁን የሰበር አመልካች እዉቅናና ፈቃድ ስጠቀምበት የቆየሁትን ለክቶ ያስቀመጠ መሆኑን እንጂ ከዉሳኔዉ ሀሳብ እና መንፈስ ዉጭ በሆነ መንገድ አልተፈፀመም፡፡

በመሆኑም በውሳኔው የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም ተብሎ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ዉድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

በበኩላችን ጉዳዩን መርምረናል፡፡ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ) ላይ በግልጽ እንደተመለከተዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉን ዉሳኔዎች በማረም ላይ የተገደበ ነዉ፡፡ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ትርጓሜ ይሰጣል፡፡ በአዋጁ በትርጉም ክፍል አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለዉ አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን፣ ህግ ያላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉን ህግ የሚጠቅስ፣ ለክርክሩ አግባብነት ያለዉ ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለዉ ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፣ በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ዉድቅ በማድረግ የተወሰነ፣ በፍርድ አፈፃፀም ሂደት ከዋናዉ ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትዕዛዝ የተሰጠበት፣ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተወሰነ፣ የአስተዳደር አካል ወይም ተቋም ከህግ ዉጭ የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ በመቃረን የተወሰነ ሲሆን ነዉ፡፡

በሌላም በኩል ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ ሲሆን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታዉን ተቀብሎ በሰበር የማየት ስልጣን የሚኖረዉ ዉሳኔዉ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ የሚቃረን ሲሆን እንዲሁም አግባብነት የሌለዉን ህግ በመጥቀስ ወይም ህግን ያላግባብ በመተርጎም የተሰጠ ዉሳኔ ሆኖ ጉዳዩም አገራዊ ፋይዳን የሚመለከት ሲሆን ብቻ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 10 (1/ሐ/ እና /መ) ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ከዚህ የምንረዳዉ የሰበር አቤቱታ የቀረበበት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ ከእነዚህ ሦስቱ ሁኔታዎች ዉጪ ባሉት ሁኔታዎች የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በሰበር የማረም ስልጣን የሌለዉ መሆኑን ነዉ፡፡

በያዝነው ጉዳይ ለአፈፃፀም ምክንያት የሆነው ውሳኔ አመልካች ለተጠሪ ያደረጉት ሥጦታ ተሰርዞ ተጠሪ የተረከቡትን ይዞታ መሬት እንዲመልሱ፤ ነገር ግን ከስጦታው በኃላ በመሬቱ ላይ የሰሩት ቤት ለመዉጫ እና መግቢያ ከሚሆን ይዞታ ጋር እንዲቀርላቸው መወሰኑ እና ይኸው ውሳኔ እስከበላይ ፍርድ ቤቶች ቅሬታ ቀርቦበት የፀና መሆኑ ግራቀኙን አላከራከረም፡፡

ፍርዱም መፈፀም ያለበት በዚሁ የውሳኔ ይዘት መሰረት መሰረት መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡ አፈፃፀሙን የመራው የስር ፍርድ ቤት በሚመለከተው ባለሙያ ተግዞ ጉዳዩን በማጣራት የቤቱን መዉጫና መግቢያ ሁኔታ፤ የአካባቢዉ ማህበረሰብ ወደ ቤተክርስትያን የሚሄድበት መንገድ መሆኑን፤ በቤቱ ፊት ለፊት ለሽንት ቤት፣ ለማድቤት፣ ለከብት ቤት እና ለከብት መኖ መከመርያ የሚያስፈልገውን ቦታም ታሳቢ በማድረግ ለመዉጫና መግቢያ የሚሆን ቦታ በማመልከት ውሳኔውን አስፈጽሟል፡፡ የፍሬ ነገር ክርክር ላይ ለመወሰን የመጨረሻ ስልጣን ያለው ይግባኝ ሰሚው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በተጨማሪ የቀረበለትን አስተያየት ሁሉ መዝኖ ተጠሪ በግብርና ስራ የሚተዳደሩ መሆኑንና መዉጫ እና መግቢያ ተብሎ የተወሰነውም ቦታ ተጠሪ ከዚህ በፊት የሚጠቀሙበት ቦታ እንጂ ተጨማሪ እንዳልተሰጠ አረጋጦ ዉሳኔውን አጽንቷል፡፡

ስለሆነም ጉዳዩ በዚህ መልኩ ታይቶ ፍርዱ መፈፀሙ ለአፈፃፀም ምክንያት የሆነውን ውሳኔ እና ህጉን መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በቀር በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል የሚሰኝ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በአጠቃላይ ከፍሲል በተጠቀሰው መልኩ የክልሉ ፍርድ ቤቶች በየደረጃው ያሳለፉት ውሳኔና ትዕዛዝ እንዲፈፀም የቀረበውን ውሳኔ ይዘት ፤ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገርና ህጉን መሠረት ያደረገ ነው ከሚባል በስተቀር መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚባል ባለመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የደብረማርቆስ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 18738 መጋቢት 06 ቀን 2014 ዓ/ም የሰጠዉን ዉሳኔ፤ የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 0154132 ጥቅምት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

15 ቀን 2015ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ፤ እንዲሁም የአማራ ብ.ክ.መ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 03-118479 ታህሳስ 21 ቀን 2015 ዓ/ም ያሳለፈው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡

2. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ/ጋ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
## የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መዝገብ ቁጥር 244505

ጥቅምት 6 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች፡----- ሽመክት አሰፋ

ገበየሁ ፈለቀ

አለማየሁ ሹናራ

ተናኜ ጥላሁን

ዘዉዲቱ ታደሰ

አመልካቾች፡-1ኛ/አቶ ተስፋዬ ፀጋስላሴ } አልቀረቡም

2ኛ/ወ/ሮ ወይንሸት ባዩ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. አቶ አብይ ስዩም

2ኛ.የቂ/ክ/ከተማውዝፍስራዎችየይዞታአስተዳደርአገልግሎትየሽግግርጊዜ-አልቀረቡም
መ/ማ/ፐ/ጽ/ቤት

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጠ

ፍርድ

ጉዳዩ የዉርስ ቤትና ይዞታን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረዉ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሆኖ አመልካቾች ከሳሾች ሆነዉ 1ኛ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ሲሆኑ 2ኛ ተጠሪ ደግሞ ጉዳዩ ከፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጣልቃ እንዲገቡ በተሰጠዉ መመሪያ መሰረት የክርክሩ አካል የሆኑ ናቸዉ ። የአመልካቾች ክስ በአጭሩ፡- የአያታችን የሚች እማሆይ ይመኙሻል ንብረት የሆነ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 11 ዉስጥ የሚገኝ በ509 ካ.ሜ ይዞታ ላይ ያረፈ የቤት ቁጥር 378 እና በዚሁ

ይዞታ ዉስጥ የሚገኝ የቤት ቁጥር 382 እና ባዶ ቦታ የነበራቸዉ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ ምንም መብት ሳይኖረዉ በአዉራሻችን የቤት ቁጥ 382 እና በባዶ ቦታዉ ላይ ቤት ሰርቶ ካርታ አዉጥቶበት እየተጠቀመበት ስለሚገኝ ይህ የቤት ቁጥር 382 እና ባዶ ቦታዉ የጋራ ወራሾች ነዉ ተብሎ እንዲወሰንልን ሲሉ ጠይቋል፡፡

1ኛ ተጠሪም በአመልከቾች በኩል የቀረበበትን ክስ መሰረት በማድረግ የመጀመሪያ መቃወሚያ በማለት ያቀረቡና በፍሬ ጉዳዩም ላይ የቤት ቁጥር 382 የሆነዉን ቤት ሟች እማሆይ ይመኙሻል በሕይወት እያሉ ለሟች አባቴ በስጦታ ሰጥተዉ ያለና 1ኛ ተጠሪ ደግሞ ሟች አባቴ ሲሞት ወራሽነት አረጋግጬ በፍርድ ቤት ዉሳኔ ያገኙት ሲሆን የቤት ቁጥር 382 የቤት ቁጥር 378 አካል ስለመሆኑ አመልካቾች ያቀረቡት ማስረጃ በሌለበት ሁኔታ ያቀረቡት ክስ ዉድቅ ይደረግልኝ ሲሉ መልስ ሰጥቷል፡፡

በዚሁ ጉዳይ ዉሳኔ ተሰጥቶ በየደረጃዉ ይግባኝ ተብሎበት ከዚያም ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ቀርቦ በመዝገብ ቁጥር 176958 ላይ የስር ፍርድ ቤቶችን ዉሳኔ በመሻር ጉዳዩ እንደገና እንዲጣራና እንዲወሰን በመመሪያ የመለሰዉ ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡

ለአሁኑ ጉዳይም መነሻ የሆነው አመልካቾች እና 1ኛ ተጠሪ ተከራክረዉ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 176958 ላይ በመመሪያ በተመለሰዉና ዉሳኔ አግኝቶ አመልካቾች በዉሳኔዉ ቅሬታ አድሮባቸዉ በመቅረቡ ምክንያት ነዉ፡፡ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 176958 ላይ ጉዳዩን ወደ ስር ፍርድ ቤት ሲመልስ የስር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት 2ኛ ተጠሪን ጣልቃ እንዲገባ በማድረግ፣ቤቶቹ እና ባዶ ቦታዉ ያለበት ሁኔታ፣ በእነ ማን ተይዞ እንደሚገኝ ፣በምን ሁኔታ ይዘው እንደሚገኙ፣የሟች ይመኙሻል ሀብት ወራሾች የትኛውን ቤት ከምን ያህል ካ.ሜ ባዶ ቦታ ጋር ይዘው እንደሚገኙ፣ከመቼ ጀምሮ ይዘው እንደሚገኙ የቤቱን ማህደር በማስቀረብ የይርጋ ክርክርን ጨምሮ ተጣርቶ እንዲወሰን ወደ ስር ፍርድ ቤት በመመሪያ ተመልሶ የፌ/መ/ደ/ ፍ/ቤትም ጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ አከራካሪው ቤት በልማት ምክንያት መፍረሱን ስላረጋገጥኩ የክሱ ምክንያት የሆነዉ ቤት የፈረሰ ስለሆነ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 280 መሰረት ክሱ ተቋርጧል ሲል ብይን ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝተዉ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ ቅሬታ ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም መዝገቡ በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀደም ሲል በተሰጠዉ ዉሳኔ ላይ ጉዳዩ በአግባቡ ተጣርቶ ያልተወሰነ በመሆኑ ተረጋገጦ እንደገና እንዲጣራ በመመሪያ

የተመለሰ ሆኖ እያለ የስር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 280 መሰረት የክስ ምክንያቱ ተቋርጧል በማለት ክሱን ዉድቅ በማድረግ የተሰጠው ብይን አግባብ አይደለም በማለት እንዲሁም አከራካሪ የሆነዉን የቤት ቁጥር 382 ን እማሆይ ይመኙሻል ለ1ኛ ተጠሪ አባት በስጦታ ስጥቷቸው የ1ኛ ተጠሪ አባት ሲሞቱ 1ኛ ተጠሪ እና ሌሎች የ1ኛ ተጠሪ አባት ወራሾች የሆኑት ይህን ቤት በመዉረስ በአሁኑ ወቅት የቤት ቁጥር 382 በሚል የተደራጀ የቤት ማህደር የሌለና የቤት ቁጥር 382 ሆነዉን ቤት የአቶ ስዩም ደስታ ወራሾች(6) ሰዎች

ባደረጉት ስምምነት ቤቱ ለሁለት በፕሮፖርሽን ተከፍሎ የቤት ቁጥር 382(1) ሆነዉ ለእነ ብስራት ስዩም ስም የተመዘገበ የሚል እና የቤት ቁጥር 382(2) ላይ ደግሞ እነ አብይ ስዩም በሚል ለሟች ስዩም ደስታ ወራሾች ለሁላቸውም ካርታ የተሰራላቸው ስለመሆኑ ከቀረበው ከቤቱ ማህደር አረጋግጫለዉ በማለት 1ኛ ተጠሪ በቤቱ ላይ በተተኪ ወራሽነት መብት ያገኙበት ስለመሆኑ የተረጋገጠ ከመሆኑ አንጻር በይዞታው ላይ አመልካቾችን ወይንም አውራሻችን ሳፈቅድለት ጋራጅ ሰርቷል በሚል አመልካቾች ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የሌለዉ መሆኑን እና 1ኛ ተጠሪ በሕጋዊ መንገድ በዉርስ ባገኘዉ ይዞታው ላይ ከ2ኛ ተጠሪ ካሳ እና ምትክ ቦታ የተቀበለበትን በመሆኑ አመልካቾች ካርታው መብታችንን ይጎዳል ሲሉ አግባብ ባለው ሂደት ባልተከራከሩበት ሁኔታ 1ኛ ተጠሪ አስቀድሞ በተተኪ ወራሽነት ቤቱን አግኝቶ በላዩ ላይም ቤት ሰርቶበት ሲጠቀምበት በነበረዉ ይዞታና ቤት በኃላም እንዲፈርስ በተደረገዉ ቤት ላይ 1ኛ ተጠሪ በህጋዊ መንገድ ያገኘዉ ስለመሆኑ ያረጋገጥኩኝ ስለሆነ 1ኛ ተጠሪ ያለ አግባብ በአመልካቾች ቤት እና ይዞታ ላይ ካሳና ምትክ ቦታ ወስዳል ሲሉ ያቀረቡትን ክስ በማስረጃ ያላስረዱ መሆኑን ተገንዝቢያለዉ በማለት የአመልካቾችን ክስ ዉድቅ በማድረግ ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡

ይህ ሰበር አቤቱታ የቀረበው አመልካቾች የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ እንዲታረም በማለት ሲሆን የቀረበው የሰበር አቤቱታም አከራካሪዎቹ ቤት ቁጥር 378፣382(1) እና 382(2) ሙሉ በሙሉ በልማት የፈረሱ መሆኑን ከሚመለከተው አካል ተጣርቷል በማለት የስር ፍርድ የሰጠው ውሳኔ የሟች ወራሾች እነማን እንደሆኑ ፣ምትክ ቦታ በምን ህጋዊ ማስረጃ እንደተሰጣቸው እና የሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔን ወደ ጎን በመተው ቦታውን የ1ኛ ተጠሪ ሟች አባት አቶ ስዩም ደስታ ቤቱን ከነይዞታዉ ከእማሆይ ይመኙሻል በስጦታ ያገኙት ስለመሆኑ በህግ አግባብ ባልተረጋጋጠበት እና የክርክሩ ጉዳይ ሊታወቅ የሚገባዉ የቤት ቁጥር 382 እና የባዶ ቦታዉ ማህደር ቀርቦ ባልተመረመረበት ሁኔታ የክሱ መነሻ የሆነዉን ቤት ቁጥር 382 እና ባዶ ቦታዉ ለ1ኛ ተጠሪ አባት በስጦታ ተሰጥቶ 1ኛ ተጠሪ ደግሞ በተተኪ

ወራሽነት ያገኙት ነው በማለት መወሰኑ በማስረጃ ያልተደገፈ እና አግባብነት ሌለዉ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን ሲሉ ጠይቀዋል፡፡

አመልካች ያቀረቡትን የሰበር ቅሬታ መነሻ ተደርጎ አመልካቾች እና 1ኛ ተጠሪ በሰ/መ/ቁ/ 176958 ላይ ተከራክረው ይህ ሰበር ችሎት የስር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የአሁኑን 2ኛ ተጠሪ በክርክሩ ጣልቃ አስገብቶ በውሳኔው ላይ በተያዙ ጭብጦች ላይ የግራ ቀኙ ክርክር በመስማት በማስረጃ የሚረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች በማስረጃ አረጋግጦ በይርጋ መከራከርያው ላይ ጭምር እንዲወስን በመለሰበት መሰረት መወሰን ሲገባው አስቀድሞ የሚታወቀውን ምክንያት አዲስ እንደተፈጠረ ምክንያት በመቁጠር የክሱ ምክንያት ተቋርጧል ሲል ፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ/ 280 በመጥቀስ ክሱ እንዲዘጋ የሰጠው ብይን ሆነ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤትም የክሱ ምክንያት

ተቋርጧል ማለቱ ስህተት እንደሆነ ከገለጸ በኋላ ራሱ ማስረጃዎችን መርምሮ እና መዝኖ የአመልካቾች ክስ የማስረጃ እና ህግ ድጋፍ ስለሌለው የስር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትን ውሳኔ ከውጤት

አንጻር ተገቢ ነው ሲል ያጸናበትን አግባብ ስነ ስርዓታዊነት እና በሰ/መ/ቁ 176958 ላይ የተሰጠውን የፍርድ ውሳኔ የተከተለ ነው ወይ ወይስ አይደለም ? የሚለዉን ለማጣራት ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀርቡ ትዕዛዝ አስተላልፏል ፡፡

1ኛ ተጠሪ ባቀረቡት መልስም አከራካሪውን ቦታ የ1ኛ ተጠሪ ሚች አባት ከሚች እማሆይ ይመኙሻል በስጦታ ስለማግኘቱ በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠና እና በይዞታው ላይም አመልካቾች ሳይቃወሙኝ ከ10 ዓመት በፊት ቤት የሰራሁ ስለመሆኑ አመልካቾም ያመኑት በመሆኑ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሊሆን የሚገባና እና በፍ/ብ/ህ/ቁ 1179 መሰረትም በይዞታዉ ላይ በሰራሁት ቤት ባለመብት ስለሆንኩ ክሱ ተቀባይነት የለውም፡፡የስር ፍ/ቤትም የሰጠዉ ዉሳኔም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰጠዉ መመሪያ መሰረት 2ኛ ተጠሪን ጣልቃ አስገብቶ፣ማህደር አስቀርቦ እና አጣርቶ የወሰነው በመሆኑ የሚነቀፍ አይደለም በማለት የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ይፅናልኝ ሲሉ መልስ ሰጥቷል፡፡

2ኛ ተጠሪ በበኩሉ ያቀረቡት መልስም አጠር ባለ መልኩ ሲታይ፡- አመልካቾች ያቀረቡት አቤቱታ በሰበር ስነ -ስርዓትን ያለተከተለ እና በሰበር መመሪያ መሰረት የቅሬታ ነጥብ

የማይገልፅ በመሆኑ ተገቢነት የሌለዉ ሲሆን የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመመሪያ በተመለሰለት መሰረት 2ኛ ተጠሪን ጣልቃ አስገብቶ መለየት ያለባቸዉን ነጥቦች ለይቶ እና አስፈላጊ ማስረጃዎችን በማስቀረብ መወሰኑ የሚከለክለው የክርክር አመራር ስርዓት የሌለ እና ቀልጣፋ ፍትህ ከመስጠት አንጻር የሚነቀፍ አይደለም ስለሆነም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ይፅናልን ሲሉ መልስ ሰጥቷል፡፡

ይህ ፍርድ ቤትም ያስቀርባል የተባለበተወን ጭብጥ ከግምት ዉስጥ በማስገባት በስር ፍርድ ቤት በተሰጠዉ ዉሳኔ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለ ወይስ የለም የሚለዉን ጉዳይ ከሕጉ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ ተመርምሯል፡፡

እኛም መዝገቡን እንደመረመርነዉ አመልካቾች የሟች አያታችን እማሆይ ይመኙሻል ከሆነዉ 509 ካ.ሜ ይዞታ ዉስጥ ያረፈ የቤት ቁጥር 382 እና ባዶ ቦታዉ ላይ ምንም ፈቃድ ሳያገኝ 1ኛ ተጠሪ ቤት ሰርቶ እየተጠቀመበት ስለሚገኝ ይህ ቤትና ይዞታ የጋራ ወራሾች ስለሆነ እንድንካፈልን ሲሉ የጠየቁትን በተመለከተ የስር ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ የአመልካቾችን ክስ ዉድቅ ካደረገ በኃላ በጉዳዩ በየደረጃዉ ይግባኝ ተጠይቆበት ከዚያም የሰበር ቅሬታ ቀርቦበት በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 176958 ላይ የስር ፍርድ ቤቶችን ዉሳኔ በመሻር ጉዳዩን እንደገና እንዲታይ በመመሪያ ሲመልሰዉ 2ኛ ተጠሪን ጣልቃ እንዲገባ በማድረግ፣ቤቶቹ እና ባዶ ቦታዉ ያለበት ሁኔታ፣ በእነ ማን ተይዞ እንደሚገኝ ፣በምን ሁኔታ ይዘው እንደሚገኙ፣የሟች ይመኙሻል ሀብት ወራሾች የትኛውን ቤት ከምን ያህል ካ.ሜ ባዶ ቦታ ጋር ይዘው እንደሚገኙ፣ከመቼ ጀምሮ ይዘው እንደሚገኙ የቤቱን ማህደር

በማስቀረብ የይርጋ ክርክርን ጨምሮ ተጣርቶ እንዲወሰን ጉዳዩን ወደ ስር ፍርድ ቤት በመምራቱ ምክንያት ጉዳዩ የተመራለት የፌ/መ/ደ/ፍ/ ቤት የክሱ ምክንያት የሆነዉ ቤት የፈረሰ በመሆኑ ክሱ በፍ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 280 መሰረት ተቋርጧል በማለት መዝገቡን በብይን ዘግቷል፡፡

በዚህ ዉሳኔ ቅር የተሰኙት አመልካቾች የይግባኝ ቅሬታ ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን የይግባኝ ቅሬታ የቀረበለት የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የክሱ ምክንያት የሆነዉ ቤት ፈርሳል በማለት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት መዝገቡን መዝጋቱ ተገቢነት የሌለዉ መሆኑን በመግለፅ በጉዳዩ ላይ ተጨማሪ ማስጃዎችን እንዲቀርቡለት በማድረግ መወሰኑ አግባብባነት ከፌ/ጠ/ፍ/ቤት የሰበር ሰሚ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 176958 ላይ በሰጠዉ መመሪያ መሰረት ነዉ ወይስ አይደለም የሚለዉን እንደሚከተለዉ ተመርምሯል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

በተያዘዉ ጉዳይ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመመሪያ ከመለሰባቸዉ ነጥብ አንዱ የአሁን 2ኛ ተጠሪ በክርክሩ አካል እንዲሆን ማድረግ ሲሆን በዚሁ መመሪያ መሰረት 2ኛ ተጠሪ የክርክሩ አካል እንዲሆን የተደረገ ሲሆን ሌላዉ ቤቶቹ ባዶ ቦታ ላይ ያሉበት ሁኔታ፣በእነ ማን ተይዞ እንደነበር፣ በምን ሁኔታ ይዘዉ እንደሚገኙ የሟች እማሆይ ይመኙሻል ሀብት ወራሾች የትኛዉን ቦታ ከምን ያህል ካ.ሜ ባዶ ቦታ ጋር ይዘዉ እንደሚገኙ እና ከመቼ ጀምሮ ይዘዉ ይሆናል የሚለዉን በባለሙያ እና የቤቱን ማህደር በማስቀረብ እንዲሁም የይርጋ ክርክርን ጨምሮ ተጣርቶ እንዲወሰን በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 343 (1) መሰረት የመለሰዉ ሲሆን የስር የፌ/ከ/ፍ/ቤት ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት በኃላ የክሱ መነሻ የሆነዉን ቤትና ቦታ የተባለዉን ለማጣራት ከክፍለ ከተማዉ መሬት አስተዳዳር ጽ/ቤት ማስረጃ እንዲቀርብለት በማድረግ እንዲሁም የቤቱን ማህደር በማስቀረብ እና በስር ፍርድ ቤት ቀደም ሲል የተሰሙትን የሰዉና የሰነድ ማስረጃ መሰረት በማድረግ በቤት ቁጥር 378 ላይ አመልካቾችና ሌሎች ወራሾች ጨምሮ ይዞታዉ የያዙና ይዞታዉም ለልማት ተፈልጎ ሲነሳ ካሳና ምትክ ቦታ የተሰጣቸዉ መሆኑን፤በክሱ ላይ የተገለፀዉ የቤት ቁጥር 382 የሆነዉ ቤት በአሁኑ ሰዓት የተደራጀ ማህደር ሌለዉ ሲሆን ይህ የቤት ቁጥር 382 የሆነዉ ቀደም ሲል የ1ኛ ተጠሪ አዉራሽ የሆኑት ሟች ስዩም ደስታ በስጦታ ከሟች እሚሆይ ይመኙሻል ያገኘዉ ስለመሆኑ እና ሟች ስዩም ደስታ ሲሞት የቤት ቁጥር 382 የሟች ስዩም ደስታ ወራሾች የአሁን ተጠሪን ጨምሮ ይህን ቤት ወርሰዉ በስምምነት እንደተካፈሉትና እነ ብስራት ስዩም በሚል በቤት ቁጥር 382 (1) ላይ የተደራጀ ማህደር መኖሩን እንዲሁም እነ አብይ ስዩም ደግሞ በቤት ቁጥር 382(2) ላይ ተደራጀ የቤት ማህደር ያለቸዉ ስለመሆኑ እና በቤቱ ላይም ላይ ካርታ ያላቸዉ መሆኑን በማጣራት 1ኛ ተጠሪ ከሟች አባቱ በዉርስ በፍርድ ቤት ዉሳኔ አግኝቶ ያለዉ እና በዚህ ይዞታ ላይ ቤት ሰርቶ ባለበት ወቅት ቦታዉ ለልማት በመፈለጉ 1ኛ ተጠሪ ባለዉ የህግ አሰራር መሰረት ለያዘዉ ህጋዊ ይዞታ ካሳና ምትክ ቦታ በ 2ኛ ተጠሪ በኩል የተሰጠዉ ስለመሆኑ እንዲሁም ለአመልካቾችም ባላቸዉ ይዞታ ልክ በቤት ቁጥር 378 ላይ ሌሎችን ወራሾች ጨምሮ ካሳና ምትክ ቦታ የተሰጣቸዉ ስለመሆኑ በማጣራት እና 1ኛተጠሪም ከላይ በተጠቀሰዉ መሰረት በዉርስ ባገኘዉ ይዞታ ላይ ቤት የሰራ እንጂ የአመልካቾችን የዉርስ ድርሻ የሆነ ባዶ ቦታ ይዞ ቤት ያልሰራበት ስለመሆኑ በማረጋገጥ አመልካቾች ያቀረቡትን ክስ ዉድቅ በማድረግ የተሰጠዉ ዉሳኔም በፌ/ጠ/ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 176958 ላይ ጭብጥ ተይዞ በመመሪያ በተመለሰዉ መሰረት የፌ/ከ/ፍ/ቤት በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በተሰጠ ዉሳኔ ላይ ባለዉ የይግባኝ ስልጣኑ የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ በማረም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰጠዉ መመሪያ መሰረት መቅረብ ያለባቸዉን ማስረጃዎች አስቀርቦ በመርመሮ አጣርቶ መወሰኑ በአግባቡ ስለሆነ የስር ፍርድ ቤት

ዉሳኔ ላይ መሰረታዊ  የህግ  ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አልተገኘም በመሆኑም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ዉሳኔ

1/ የፌ/ከ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 293558 ላይ በቀን 20/6/2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ በፌ/ጠ/ፍ/ቤት የሰበር ስነ -ስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1)(ሀ) መሰረት ፀንቷል፡፡

2/ ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ወገኖች ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ም

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
## የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 244507

ጥቅምት 7 ቀን 2017 ዓ.ም

**ዳኞች** ፡-ሽመልስ አሰፋ

ገበየሁ ፊለቀ

አለማየሁ ሹናራ

ተናኜ ጥላሁን

ዘውዲቱ ታደሰ

አመልካች፡- አቶ ሽመልስ አሸክባ - አልቀረበም

ተጠሪዎች፡- 1. ድንበሬ ጌታቸው - አልቀረቡም

2. ኮንስታብል መላኩ መሳይ - ቀረቡ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ሲሆን ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች መጋቢት 18 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 420967 ጥር 18 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጧቸው ፍርዶች መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው መነሻነት ነው፡፡

ክሱ 2ኛ ተጠሪ በሌለሁበት የተደረገው የሽያጭ ውል እንዲፈርስ እንዲሁም የቤቱ ግምት በውርስ ድርሻዬ ልክ እንዲከፈለኝ ይወሰንልኝ በማለት የቀረበ አቤቱታን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በኦሮሚያ የግራር ጃርሶ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር 2ኛ ተጠሪ ከሳሽ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

2ኛ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት አቅርበውት የነበረው ክስ ይዘት ባጭሩ ፡- እናቴ የሆነችው 1ኛ ተጠሪ በሟቹ አባታችን አቶ መሳይ ንጉሴ ስም ተመዝግቦ ያለውን ቤት/ይዞታ እኔ በሌለሁበት አመልካች 1ኛ ተጠሪን በማታለል አጎቱ አቶ ካፍትሙ ደሜ የሚባለውን ሰው ፎቶ ስሙን መላኩ መሳይ ብሎ በመታወቂያ ወረቀት ላይ በመለጠፍ እኔ በውሉ ውስጥ እንዳለሁ በማስመሰል በሌለሁበት በ 2012 ዓ.ም አመልካች የንብረቱን ስመሀብት ከ1ኛ ተጠሪ ወደ ራሱ ስም አዛውሯል፡፡ የቤቱ ስመሀብት ወደ አመልካች በመዛወሩ ምክንያት ከሟች አባቴ የማገኘውን የውርስ ድርሻ እንዳጣ ስላደረጉኝ በአመልካች እና በ1ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገው ውል እንዲሰረዝልኝ እንዲሁም ይዞታው ግምቱ ብር 900,000 (ዘጠኝ መቶ ሺ.ህ) የሚያወጣ ስለሆነ 1ኛ ተከሳሽ የውርስ ድርሻዬን ብር 112,500 (አንድ መቶ አስራሁለት ሺህ አምስት መቶ) እንድታካፍለኝ እንዲሁም ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ እንዲከፍሉኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

1ኛ ተጠሪ በጽሁፍ መልስ ሳላላቀረቡ በጽሁፍ መልስ የማቅረብ መብታቸው ታልፏል፡፡

አመልካች በሰጡት መልስ በፍቼ ከተማ አስተዳደር ማኔጅመንት እና ልማት ጽ/ቤት ቀርበን 1ኛ ተከሳሽ እና ልጆቿ ስማቸውንና መልካቸውን የማላውቃቸው ጽ/ቤቱ ማንነታቸውን መታወቂያ አይቶ በመለየት ከአመልካች ጋር በቀን 11/06/2012 ዓ.ም የመኖሪያ ቤት ሽያጭ እና ግዢ ውል በብር 200,000 (ሁለት መቶ ሺ.ህ) ሸጠውልኝ ገንዘቡን ወስደዋል፡፡ ተጠሪ ይህንን ውል ያደረኩት 1ኛ ተጠሪን በማታለል ሳይሆን 1ኛ ተጠሪ ውሉን የፈረሙት ሰዎች ልጆቼ ናቸው በማለት በቅንነት ተስማምተን የፈጸምኩ በመሆኑ ከ3ኛ ወገን ጋር ተያይዞ ለሚመጣ ኃላፊነት ተጠያቂ አይደለሁም፡፡ 1ኛ ተጠሪ አመልካች ይህንን የሽያጭ ውል በምፈርምበት ጊዜ መላኩ ልጄ ነው ብላ የተናገረች እና ከልጆቹም ጋር ቀርባ ውሉን የፈረመች በመሆኑ የቀረበው ክስ የህግ ድጋፍ የለውም ተብሎ ውድቅ በመሆን ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ እንዲከፈለኝ ይወሰንልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍሬ ጉዳዩን በማስረጃ የማጣራትና የመመዘን ስልጣን ያለው የስር ፍ/ቤት የግራ ቀኙን የጽሁፍና የቃል ክርክር ከሰማና ለጉዳዩ እልባት ለመሥጠት ተገቢ ናቸው ያላቸውን ጭብጦች ከለየ በኂላ የቀረበለትን የሰነድ እና የሰው ማስረጃዎች ከክሱ ጋር በማገናዘብ መርምሮ 1ኛ ተጠሪ አልማዝ መሳይ፣ ድሪባ መሳይ፣ መላኩ መሳይ፣ ታደሉ መሳይ የተባሉት ልጆቿ አሳዳጊ መሆኗን በመ/ቁ 24132 በቀን 18/10/2007 ዓ.ም በማረጋገጥ በፍቼ ከተማ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ከአራቱም ልጆቿ ጋር በጋራ በመቅረብ፣ በቀን 11/06/2012 ዓ.ም በተደረገው የሽያጭና ግዥ ውል ውስጥ በመሳተፍና የስም ዝውውሩን የፈጸመች ስለመሆኗ ከቀረበው የጽሁፍ ማስረጃ እና ከተሰማው የሰው ምስክር የተረጋገጠ መሆኑን በመግለጽ፤ በአንጻሩ አመልካች በውሉ ላይ አልተሳተፍኩም ፊርማዬ እና ፎቶዬን ካፍታሙ ደምሴ በሚባለው ሰው በማስመሰል ተደርጓል ቢልም በማስረጃ ያረጋገጠው ነገር ስለሌለ ይህ ከሆነ ደግሞ የተደረገው የሽያጭና ግዢ ውል ጉድለት አለው ወይም ስህተት ተደርጓል ተብሎ ውል የሚሻርበት ወይም የሚፈርስበት የህግ ድጋፍ የለም በማለት የከሳሽን ክስ ውድቅ በማድረግ በማለት ወስኗል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

2ኛ ተጠሪ ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱ ይግባኙን ከመረመረ በኋላ ይግባኙ መልስ ሰጪ የሆኑትን የአሁን አመልካችን እና 1ኛ ተጠሪዋን ያስቀርባል በማለት በይግባኙ ላይ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ 1ኛ ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን የውርስ ንብረት የልጆቿ አሳዳጊ ሆና ባለበት የአባታቸውን ውርስ ንብረት ለመሸጥ በፌ/ጠ/ፍ/ቤት/ሰ/ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 54827 እና 54129 በተሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሰረት ስልጣን የላትም፡፡ 1ኛ ተጠሪ ያላት ስልጣን የልጆቹ አሳዳጊ እንጂ የልጆቹ ንብረት አስተዳዳሪ ባለመሆኗ ንብረቱን መሸጧ ትክክል አይደለም፡፡ የልጆቹ አሳዳጊ ነኝ በማለት የቤቱን ሽያጭ ለአመልካች የሸጠች ስለሆነ ጥፋተኛ 1ኛ ተጠሪ እንጂ አመልካችን የማይመለከተው በመሆኑ 1ኛ ተጠሪ ለአመልካች 200,000 (ሁለት መቶ ሺህ) ብር ስለሸጠች ከዚህ ገንዘብ ውስጥ የሚስትነቷን ድርሻ 50% ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ) ከተቀነሰ በኋላ የሚቀረውን ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ) 2ኛ ተጠሪን ጨምሮ ለአራቱም ልጆች ለእያንዳንዳቸው ብር 25,000/ሃያ አምስት ሺ/ ልትከፍላቸው ይገባል፡፡ ወጪና ኪሳራን በተመለከተም 1ኛ ተጠሪ ለ2ኛ ተጠሪ 2,000 (ሁለት ሺህ) ብር ልትከፍል ይገባል ሲል በመወሰን የስር ወረዳ ፍ/ቤቱን ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348 መሰረት ሽሮ የሥር ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ሳይሰጥበት ያለፈውን የአሁን 2ኛ ተጠሪ የውርስ ድርሻ ላይ ውሳኔ በማሳረፍ የአሁን አመልካችን ተጠያቂነት የለበትም በማለት በነጻ በማሰናበት በውጤት ደረጃ ውሉን የማጽናት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁን 2ኛ ተጠሪ ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት የፍትሐብሄር ችሎት ያቀረቡትን ይግባኝ ፍ/ቤቱ ከመረመረ በኋላ የወረዳው ፍ/ቤት አመልካች ባለንብረት ከሆነው ሰው ጋር ውል የፈረመው በአካልና በገጽታ እንደማያውቀው እየገለጸ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ጥፋት የለብኝም ማለቱ እርስ በእርሱ የሚጋጭ ሲሆን የከፍተኛው ፍ/ቤት 2ኛ ተጠሪ እንዲፈርስለት እየጠየቀ ያለው ውል እና ክርክር ያስነሳው ጉዳይ የ2012 ዓ.ም ውል እንጂ የ2007 ዓ.ም ውል ያለመሆኑን አልተገነዘበም እንዲሁም የወረዳው ፍ/ቤት አሁን ክርክር ባስነሳው ውል ላይ ነው እንጂ በመጀመሪያው ውል ላይ ክርክር ባለመደረጉ የከፍተኛው ፍ/ቤት በተደረገው ክርከር ውሳኔ መስጠት ያለበትን ወደጎን በመተው ለአሁኑ ጉዳይ ምክንያት ያልሆነውን ውል በመመርመር የሰጠው ውሳኔ ስህተት ነው፡፡ 2ኛ ተጠሪን በማስቀረት የተፈጸመው የሽያጭ ውል የጋራ ንብረት በሆነው የውርስ ሀብት ላይ የተደረገ ነው፡፡ የጋራ ንብረት ደግሞ የባለይዞታነት መብት ያላቸው ሁሉ ሙሉ ፍላጎትና ፍቃድ ሳይኖር ውሉ መደረግ እንደማይችል በፍ/ህ/ቁ 1266 ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ስለዚህ ይግባኝ ባዩ በውርስ ድርሻ ባለው የቤት ንብረት ላይ ፍላጎቱን እና ፍቃዱን ሳይሰጥ 1ኛ ተጠሪ ከወራሾች ጋር የሸጠችው ቤት እና አመልካች የገዛው የይግባኝ ባዩን የባለይዞታነት ፍቃድ እና ፍላጎት ስላለው ውሉ መፍረስ አለበት በሚል ወስኖ፣ የሰሜን ሸዋ ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲሁም የግራር ጃርሶ ወረዳ ፍ/ቤት የሰጡትን ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ሽሮታል፡፡

አመልካች ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም ውሳኔው ሳይለወጥ ቀርቷል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አመልካች መጋቢት 18 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት አቤቱታ ይህን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ሲሆን ይዘቱም አመልካች በቀን 11/06/2012 ዓ.ም በተጻፈ የቤት ሽያጭ ውል መሰረት ቤቱን ስገዛ 1ኛ ተጠሪ የሟች የአቶ መሳይ ንጉሴ ልጆች ናቸው የተባሉትን አራት ልጆች ይዛ በፍቼ ከተማ መሬት ልማት እና ማጅመንት ጽቤት ቀርባ ልጆቼ እነዚሁ ናቸው በማለት ልጆቹንም የማንነት መገለጫ የሆነውን መታወቂያቸውን ይዛ በመቅረብ የሚመለከተው የመንግስት አካልም ማንታቸውን በማረጋገጥ እና ቤቱን ከሚመለከቱ ሰነዶች ጋር በማመሳከር ውሉን እንድንፈጽም በማድረግ የቤቱ ስመ ሀበት በእኔ ስም የዞረ መሆኑን እንዲሁም ቤቱን በሽያጭ ካገኘሁ በኋላ ተጨማሪ ወጪዎችን አውጥቼ ተጨማሪ ቤቶችን በቦታው ላይ የሰራሁ መሆኑ ተረጋግጦ ባለበት ሁኔታ ውሉ እንዲፈርስ መወሰኑ አግባብነት ያለው አይደለም፡፡ እኔ አመልካች ቤቱን የገዛሁት የንብረቱ ባለሀብቶች የአሁን 1ኛ ተጠሪ እና በሚመለከታቸው አካል ዘንድ ይዛቸው የቀረበቻቸው ልጆቿ መሆናቸውን በማመን በቅን ልቦና ውሉን የፈፀምኩ መሆኑን በሥር ወረዳ እና ከፍተኛ ፍ/ቤቶች ተጣርቶ እያለና በቅን ልቦና የተደረገ የቤት ሽያጭ ውል ደግሞ መፍረስ እንደሌለበት ይህ ችሎትም በመ.ቁ. 47378 (ቅጽ 10) ላይ አስገዳጅ ውሳኔ ሰጥቶ ባለበት ሁኔታ ውሉ እንዲፈርስ የተሰጠው የጠቅላይ ፍርድ ቤቱና የሰበር ሰሚው ችሎት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡

በሌላ በኩል የዚህ ንብረት ባለቤት የአሁን 1ኛ ተጠሪ እና የአሁን 2ኛ ተጠሪ ጨምሮ አራቱ የሟች የአቶ መሳይ ንጉሴ ልጆች መሆናቸውን በሥር ፍ/ቤቶች በተደረገ ማጣራት የተረጋገጠ እና የታመነ ጉዳይ ነው፤ የንብረቱ 50% ደርሻ የ1ኛ ተጠሪ ፣ ቀሪው 50% ደግሞ 2ኛ ተጠሪን ጨምሮ የአራቱ ልጆች ድርሻ የሸጡልኝ በመሆኑ ውሉ ይፍረስ ቢባል እንኳን በፍ/ህ/ቁ 1260(1) የአንድ ንብረት የጋራ ሀብት ድርሻውን ለ3ኛ ወገን ማስተላልፍ እንደሚችል በተደነገገው መሰረት የሌሎችንም ድርሻ ጨምሮ ውሉ እንዲፈርስ ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ መሰረተዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔን በመሰረዝ የወረዳ እና የከፍተኛ ፍ/ቤቱ የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 348(1) መሠረት እንዲያጸናል እና ወጪና ኪሳራዬን እንዲወስንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የሽያጭ ውሉ በሻጮች ያልተካደና ስመሀብቱም ወደ አመልካች የተዛወረ መሆኑ ባልተካደበት ሁኔታ ውሉ እንዲፈርስ የተሰጠው ውሳኔ በተመሳሳይ ክርክሮች ላይ በሰበር ችሎቱ ከተሰጠው ውሳኔ አንጻር አንጻር አግባብነት ያለው ስለመሆኑ ሊመረመር የሚገባ ሆኖ በመገኘቱ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

1ኛ ተጠሪ ሐምሌ 10 ቀን 2015 ዓ.ም በተጻፈ የሰጡት መልስ ይዘት ባጭሩ አመልካች ቤቱን በሚገዛበት ወቅት የ2ኛ ተጠሪን ድርሻ አልሸጥም እሱ ሲመጣ ይሁን ስለው የአመልካች አጎት የሆነውን አቶ ካፍታሙ ደሜ የተባለውን በ2ኛ ተጠሪ ምትክ አቅርቦ በፍቼ ከተማ መሬት ልማት አስተዳደርና ማኔጅመንት አቅርቦ የማታለል ውል ፈጸመ እንጂ በቅን ልቦና የፈጸመው ውል አይደለም፡፡ የአሁን አመልካች ባለቤትና የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ የአጎት ልጆች አብረው ያደጉ በመሆናቸው 2ኛ ተጠሪ ልዩ ሀይል መሄዱን እያወቀ የገዛ በመሆኑ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም፡፡ አመልካች የግዢውን ገንዘብ አልሰጠኝም፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አራቱ ልጆች ባሉበት ያለውን በተመለከተ ያሉት ሶስት ልጆች ናቸው በዛን ጊዜ ፍቃዳቸውን ለመስጠት ዕድሜያቸው ለአቅመ አዳም ያልደረሱ በመሆናቸው የሰጡት ፍቃድ ስለሌለ በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰ/መ/ቁ 47378 ሥር አይካተትም፡፡ እኔ ልጆቹን የማሳደግ ስልጣን እንጂ ንብረቱን የመሸጥና የመለወጥ ስልጣን ስለሌለኝ ያለ 2ኛ ተጠሪ እውቅና እና ፍቃድ ውጪ የተሸጠው ቤት ውሉ እንዲፈርስልኝ እና 2ኛ ተጠሪ በቦታው ላይ ሰርቶት የነበረው ሶስት ክፍል ቤት በመፍረሱ ግምቱ ይከፈለኝ በማለት በጠየቀው መሰረት አመልካች ያፈረሰውን የውርስ ድርሻ ከፍሎ የሰራበትን ቤት በራሱ ኪሳራ አፍርሶ እንዲወስድስና ቦታውን እንዲለቅለት ቢወሰን አልቃወምም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ የወሰነውን ውሳኔ 2ኛ ተጠሪ እንዲጸድቅለት ይወሰንለት በማለት ተከራክረዋል፡፡

2ኛ ተጠሪ ሐምሌ 11 ቀን 2015 ዓ.ም በተጻፈ የሰጡት መልስ ይዘት ባጭሩ 2ኛ ተጠሪ የአባቴ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ስሆን ከአመልካቹ ባለቤት ጋር የወንድማማቾች ልጆች ቤተሰብ ሆነን አብረን ያደግንና የምንተዋወቅ ሆኖ እያለ 2ኛ ተጠሪ ለኦሮሚያ ፖሊስ ስልጠና መሄዴን እያወቀ በእኔ ቦታ ወንድሙን አቶ ካፍታሙ ደሜን በፍቼ ከተማ መሬት ማኔጅመነት አቅርቦ 2ኛ ተጠሪ ይህ ነው ብሎ ውሉን አስገብቶ መ/ቤቱን አታሎ መብቴን በሚጋፋ መልኩ የተገባ ውል እንጂ በቅን ልቦና ባለማወቅ የተደረገ ውል ባለመሆኑ ውሉ ውድቅ ተደርጎልኝ አባቴ የሰራውን ቤት ግምቱን ድርሻዬን ብር 900,000 (ዘጠኝ መቶ ሺህ ብር) እንዲከፍለኝ፤ የቤቱን ቦታ ለቆ መብቴን ሆን ብሎ ለመጋፋት የተደረገው ውል ፈርሶልኝ የሰራውን ቤት በራሱ ኪሳራ አፍርሶ እንዲለቅልኝ ፡፡ በስር ፍ/ቤት እና በከፍተኛ ፍ/ቤት ተሽሮ የኦሮሚያ ጠቅላ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ትክክል ስለሆነ መሰረታዊ የህግ ስህተት የሰለበትም ተብሎ እንዲጸድቅልኝ ለክርርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ አመልካች እንዲከፈልፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካች የመልስ መልስ ባለማቅረባቸው የመልስ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

ግራቀኙ ክርክርና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፣ ለሰበር አቤ ቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ህጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ የቻልነው ጉዳዩ የቀረበለት ፍሬ ጉዳዩን በማስረጃ የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው የስር ወረዳ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን የጽሁፍና የቃል ክርክር ከሰማ በኋላ 1ኛ ተጠሪ ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነውን ንብረት በውርስ መተላለፍ ያለበትን የባለቤቷን ድርሻ በወራሾች ተሳትፎ ለአመልካች ሸጣለች? ወይስ አልሸጠችም? 2ኛ ተጠሪ በሽያጭና ግዢ ውል ውስጥ በአካል ሳይሳተፍ በማስመሰል ካፍታሙ ደምሴ የተባለው ሰው ፎቶ እና ፊርማ ተሳትፎበታል? ወይስ አልተሳተፈበትም? ሁሉም ወራሾች ባልተሳተፉበት ቦታ ውሉ የተፈጸመ ከሆነ ውሉ መፍረስ አለበት ?ወይስ የለበትም? አመልካች በውሉ ምክንያት ሊጠየቅበት ይገባል ? ወይስ አይገባም? ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት ግምቱ ምን ያህል ገንዘብ ያወጣል? አመልካች በሽያጭና ግዢ ውል ከያዘ በኋላ ተጨማሪ ምን ምን አውጥቶበታል? የወጣበት ግምት ስንት ነው? የሚለውን ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ጭብጦች ለይቶ በመያዝ የቀረበለትን የሰነድ እና የሰው

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ማስረጃዎች ከክሱ ጋር በማገናዘብ ከመረመረ በኋላ 1ኛ ተጠሪ አልማዝ መሳይ፣ ድሪባ መሳይ፣ መላኩ መሳይ፣ ታደሉ መሳይ የተባሉት ልጆቿ አሳዳጊ መሆኗን በመ/ቁ 24132 በቀን 18/10/2007 ዓ.ም. ከተሰጠ የፍርድ ቤት ውሳኔ በማረጋገጥና በፍቼ ከተማ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ከአራቱም ልጆቿ ጋር በጋራ በመቅረብ፣ በቀን 11/06/2012 ዓ.ም በተደረገው የሽያጭና ግዥ ውል ውስጥ በመሳተፍና የስም ዝውውሩን የፈጸመች ስለመሆኗ ከቀረበው የጽሁፍ ማስረጃ እና ከተሰማው የሰው ምስክር የተረጋገጠ መሆኑን በመግለጽ፤ በአንጻሩ አመልካች በውሉ ላይ አልተሳተፍኩም ፊርማዬ እና ፎቶዬን ካፍታሙ ደምሴ በሚባለው ሰው በማስመሰል ተደርጓል ቢልም በማስረጃ ያረጋገጠው ነገር ባለመኖሩ የክርክሩ ምክንያት የሆነው የሽያጭና ግዢ ውል ጉድለት አለበት የሚያሰኝ ህጋዊ ምክንያት ባለመኖሩ ውሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት የከሳሽን ክስ ውድቅ በማድረግ በማለት ወስኗል።

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም ከአሁን አመልካች አንጻር ጥፋት የሌለበት በመሆኑ ውሉ ሊፈርስ አይገባም የሚለውን የሥር ፍርድ ቤቱን ውሳኔ በውጤት ደረጃ በማጽናት፣ ውሉ ቢጸናም 2ኛ ተጠሪዋ የልጆቹ አሳዳጊ ነኝ በማለት ቤቱን ለአመልካች የሸጠች ስለሆነ ጥፋተኛ 1ኛ ተጠሪ እንጂ አመልካችን የማይመለከተው ነው በማለት የአሁን 2ኛ ተጠሪ ከውርስ ድርሻው የሽያጭ ገንዘብ ላይ ሊያገኝ የሚገባውን ድርሻ በሚመለከት በሥር ፍርድ ቤቱ ሳይወሰን መቅረቱን በማረም 1ኛ ተጠሪ ለአመልካች 200,000 (ሁለት መቶ ሺህ) ብር ስለሸጠች ከዚህ ገንዘብ ውስጥ የሚስትነቷን ድርሻ 50% ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ) ከተቀነሰ በኋላ የሚቀረውን ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ) 2ኛ ተጠሪን ጨምሮ ለአራቱም ልጆች ለእያንዳንዳቸው ብር 25,000/ሃያ አምስት ሺ/ ልትከፍላቸው ይገባል። ወጪና ኪሳራን በተመለከተም 1ኛ ተጠሪ ለ2ኛ ተጠሪ 2,000 (ሁለት ሺህ) ብር ልትከፍል ይገባል በማለት በሰጠው ውሳኔ 2ኛ ተጠሪን ጨምሮ አራቱም ልጆች ቀርበው የሽያጭ ውሉን ስለመፈረማቸው ውሉ የሚያስረዳ መሆኑ ከመረጋገጡ በቀር፤ በአሁን 2ኛ ተጠሪ ስም ሌላ ግለሰብን አመልካች አታሎ አቅርቦ አስፈርሟል የሚለው ፍሬ ነገር በማስረጃ የተረጋገጠ አለመሆኑን ከሥር ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ይዘት መረዳት የተቻለ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ 1ኛዋ ተጠሪ የ2ኛው ተጠሪን የውርስ ድርሻ ለመሸጥ መብት ሳይኖራቸው ሸጠዋል ቢባል እንኳ የአሁን አመልካች በንብረቱ ላይ መብት ያላቸው የተባሉት ሁሉ ቀርበው ውል የተፈጸመ መሆኑን ተረድተው 1ኛ ተጠሪዋ እና አራት ወራሾች ነን ያሉት በውሉ ላይ እንዲፈርሙ ተደርጎ የሽያጭ ውሉ የተፈጸመ ከመሆኑ አንጻር ቤቱን ገዢ የሆኑት የአሁን አመልካቹ የቅን ልቦና ተዋዋይ መሆናቸው በመረጋገጡ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰ/መ/ቁ. 47378 ከውርስ ጋር በተያያዘ በቤት ላይ ህጋዊ መብት የሌለው ሰው ሽያጭ አከናውኖ ሲገኝ ትክክለኛው ባለሀብት መብቱን ሊጠይቅ የሚችለው ተገቢውን ገዥ ሣይሆን ሻጩን ስለመሆኑ በመግለጽ ከሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም አንጻር ይግባኝ ሰሚው የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህንኑ የሰበር አስገዳጅ ትርጉም መሠረት በማድረግ የቅን ልቡና ተዋዋይ የሆኑት የአሁን አመልካች ጥፋት የሌለባቸው መሆኑን በውሳኔው ላይ በማመልከት ከሽያጩ ገንዘብ ላይ 1ኛ ተጠሪዋ የ2ኛ ተጠሪውን ድርሻ እንዲከፍሉ በመወሰን አመልካችን በተመለከተ ተጠያቂነት የለበትም በማለት በነጻ በማሰናበት የሽያጭ ውሉን የማጽናት ውጤት ያለው ውሳኔ መስጠቱ ተገቢ በህግ መሠረት የተወሰነ ከመሆኑ በቀር የሚነቀፍበት የህግ መሠረት ያለመኖሩን ተረድተናል።

ሆኖም ይግባኝ ሰሚው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአሁን 2ኛ ተጠሪ በውሉ ላይ አልተሳተፍኩም ፊርማዬ እና ፎቶዬን ካፍታሙ ደምሴ በሚባለው ሰው በማስመሰል ተደርጓል ቢልም በስር ፍርድ ቤት በማስረጃ ያረጋገጠው ነገር ያለመኖሩን ከግምት ሳያስገባ የ2ኛ ተጠሪውን ክርክር ብቻ መሠረት በማድረግ የአሁን 2ኛ ተጠሪ የውርስ ድርሻ ባለው የቤት ንብረት ላይ ፍላጎቱን እና ፍቃዱን ሳይሰጥ 1ኛ ተጠሪዋ ከሌሎች ወራሾች ጋር በመሆን ለአሁን አመልካች ንብረቱን የሸጠችበት የሽያጭ ውል ሊፈርስ ይገባል በማለት የሰጠው ውሳኔ የማስረጃ ምዘና ስህተት ያለበት በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ እያለ፣ ይህንን ስህተት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ሳያርም መቅረቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ነው ብለናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 397488 በጥቅምት 29 ቀን 2015 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 420967 በጥር 18 ቀን 2015 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 ተሽሯል ::
2. የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 74142 በጥር 18 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ጸንቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ::

መ/ዐ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

<u>ማስታወሻ</u>፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መዝገብ ቁጥር - 244551

ቀን - 05/02/2017

ዳኞች - ሽመክት አሰፋ

ገበየሁ ፈለቀ

አለማየሁ ሹናራ

ተናኘ ጥላሁን

ዘውዲቱ ታደሰ

አመልካቾች - 1. አቶ ተሾመ ጎሹ

2. አቶ መሀመድ አማን

3. ወ/ሮ የሺ ወልዴ

4. አቶ ከተማ ድንቅነህ

} የቀረበ የለም

ተጠሪ - የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ነ/ፈ/ትእትስት -ቀረቡ

መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው ለምርመራ ስለሆነ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ጉዳዩ የተጀመረው በፌድራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን በስር ፍርድ ቤት አመልካቾች ከሳሾች ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾች በተጠሪ ላይ ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ ከ 3ኛ አመልካች ውጪ ያሉት አመልካቾች በተጠሪ ድርጅት በጥበቃ ስራ የተቀጠሩ መሆናቸውን 3ኛ አመልካች በፅዳት የስራ መደብ ተቀጥራ እስከ መስከረም 30 ቀን 2015 ኢ.ም ድረስ ሲሰሩ መቆየታቸውን ተጠሪ ድርጅት ያለፍላጎታችን በኤጀንሲ ተደራጁ በማለት ከአሰሪና ሰራተኛ ህግ ውጪ ያለማስጠንቀቂያ ከጥቅምት 1 ቀን 2015 ኢ.ም ጀምሮ የስራ ውል በማቋረጥ ከስራ ያሰናበተን በመሆኑ የስራ ውል የተቋረጠው ህገወጥ ስለሆነ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ የስራ ስንብት ክፍያ የስድስት ወር ደሞዝ፣ የካሳ ክፍያ ያልተጠቀሙበት የአመት እረፍት ወደ ገንዘብ ተለውጦ እንዲከፍል በጠቅላላው ብር 318,939.20 (ሶስት መቶ አስራ ስምንት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ብር ከሀያ ሳንቲም) እንዲከፍል እንዲወሰንልን የሚል ነው፡፡ ተጠሪ ለክሱ የሰጠው መልስ ይዘት የከሳሾች የስራ ውል የተቋረጠው አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀፅ 28(3)(ሐ) መሰረት የአገልግሎት አሰጣጥን ተደራሽ ለማድረግ የእውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር በማድረግ የአገልግሎት አሰጣጥን ለማሳለጥ እና ለማዘመን፣ የአሰራር ክህሎትን እና የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ለማሳደግ የተቋሙ የአስተዳደር ጫና ለመቀነስ ሲል በርካታ የስራ ዘርፎችን አውት ሶርስ በማድረግ በ 3ኛ ወገን በውል ለማሰራት መመሪያ አዘጋጅቶ ሚያዚያ 3 ቀን 2013 ኢ.ም በስራ አመራር ቦርድ በማፀደቅ እና ተገቢው ዝግጅት ሲያደርግ ቆይቶ ወደ ትግበራ ገብቷል፡፡ በስራ ዘርፉ ያሉት ሰራተኞች በየስራ ዘርፉ በማህበር ተደራጅተው ፍቃድ ሲያቀርቡ ለማህበራቱ ቅድሚያ በመስጠት ለማቋቋሚያ የፋይናንስ እና የማቴሪያል ድጋፍ በማድረግ ስራውን በውል ተረክቦ እንዲሰራ ሁኔታዎችን አመቻችቷል፡፡ በዚህ መሰረት የጥበቃና ፅዳት የስራ መደብ ላይ በኢትዮጵያ የጥበቃና የፅዳት አገልጎሎት አ/ማ እና የነገ ተስፋ ጥበቃና ፅዳት ሰራተኞች አ/ማ በሚል ተቋቁመው ስራውን በውል በመረከባቸው ምክንያት የከሳሾች የስራ ውል በህግ አግባብ ተቋርጧል፡፡ ከሳሾች ይሰሩበት የነበረው የስራ መደብም በስራ አመራር ቦርድ ውሳኔ ተሰርዟል፡፡ የከሳሾች የስራ ውል የተቋረጠው በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀፅ 28(3)(ሐ) እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 38435 በሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሰረት ስለሆነ የስራ ውሉ የተቋረጠው በህጋዊ መንገድ ስለሆነ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ካሳ፣ የስራ ስንብት የአገልግሎት ክፍያ የምከፍልበት ምክንያት የለም ክሱ ውድቅ እንዲደረግ በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ የፅሁፍና የቃል ክርክር ከተጠናቀቀ በኃላ ፍርድ ቤቱ የከሳሾች የስራ ቅጥር ውል የተቋረጠው በህግ አግባብ ነው ወይስ ከህግ ውጪ ተከሳሽ ከሳሾችን ውዝፍ ደሞዝ ከፍሎ ወደ ስራ

ሊመልስ ይገባል ወይስ የጠየቁትን ክፍያዎች ለከሳሾች ሊከፍል ይገባል ወይስ አይገባም የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ መዝገቡን መርምሮ ተከሳሽ ከስራ ያሰናበተበት ምክንያት

የተከሳሽ ድርጅት የጥበቃና የፅዳት ስራዎች በ 3ኛ ወገን እንዲሰራ በውል በመስጠቱ ምክንያት በመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 38435 አስገዳጅ የህግ ትርጉም በሰጠው መሰረት የስራ ውል የተቋረጠው ህጋዊ ነው፡፡ ተከሳሽ ማስጠንቀቂያ ለከሳሾች ልኮ ከሳሾች ማስጠንቀቂያ ለመውሰድ ፍቃደኛ ያለመሆናቸው የተረጋገጠ ስለሆነ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ሊከፍል አይገባም፡፡ ሰራተኛ የስራ ስንብት ክፍያ ሳያገኝ የስራ ውል እንዲቋረጥ እና ሰራተኛ ለድንገተኛ ችግር እንዲጋለጥ ማድረግ የአዋጁ አላማ አይደለም፡፡ ለብዙ አመታት ያገለገለ ሰራተኛ የጡረታ ተጠቃሚ ሳይሆን በአሰሪው አነሳሽነት ለአሰሪው ጥቅም ተብሎ የስራ ቅጥር ውል የሚቋረጥበት ሰራተኛ የስራ ስንብት ክፍያ ሊያገኝ የሚገባ ስለሆነ ተከሳሽ የስራ ስንብት ክፍያ ሊከፍል ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት የይግባኝ ቅሬታ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ ፍርድ ቤቱም በመዝገብ ቁጥር 294246 በቀን 01/07/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በመሻር ተጠሪ የስራ ስንብት ክፍያ ሊከፈል አይገባም በማለት ሽሮታል፡፡

የአሁን ሰበር ቅሬታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካቾች ቅር በመሰኘታቸው ነው፡፡ የአመልካቾች ሰበር ቅሬታ ይዘት በአጭሩ አመልካቾች የቤተሰብ አስተዳዳሪዎች በመሆናችን በቤተሰቦቻችን ላይ የከፋ ጉዳት በመድረሱ በተጠሪ ድርጅት ውስጥ ከ 5 አመት በላይ በታማኝነት እና በቅንነት ስንሰራ የቆየን በመሆናችን በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀፅ 39(ለ) መሰረት በአሰሪው አነሳሽነት የስራ ውል ሲቋረጥ ሰራተኛው ከአሰሪው የስራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት እንዳለው የሚደነግግ በመሆኑ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሮ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲፀናልን የሚል ነው፡፡ ይህ ችሎት አመልካቾች በተጠሪ ተቋም በፅዳትና በጥበቃ ስራ መደብ ላይ ተቀጥረው ለረጅም አመታት ያገለገሉ ሲሆን በተጠሪ አነሳሽነት ለተጠሪ ጥቅም ሲባል የስራ መደቦች ለሶስተኛ ወገን በመተላለፉ (አውት ሶርስ) በመደረጋቸውና የስራ መደቦቹ በመሰረዛቸው የአመልካቾች የስራ ውል የተቋረጠው በህግ አግባብ ስለሆነ የሚከፈላቸው ክፍያ የለም ተብሎ የተወሰነበት አግባብ ከአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 28(3) መሰረት በአብላጫ ድምፅ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ የበኩሉን መልስ በ 14/12/2015 ዓ.ም በተፃፈ 04 ገፅ አቅርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡ ፍሬ ቃሉ በአጭሩ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀፅ 28(1)(መ) አላማው የተቋሙን የገንዘብ አቅም መጨመር ተቋሙን ከኪሳራ ማዳን በመሆኑ በዚህ

መሰረት ለተሰናበተ ሰራተኛ የሚከፈል የስራ ስንብት ክፍያ የለም፡፡ የስራ ውል መቋረጡ ህጋዊ በመሆኑ የስራ ስንብት ክፍያ ሊከፈል አይገባም፡፡ የስራ ውል የተቋረጠው ስራ መደቡ አውት ሶርስ በመደረጉ ለሌላ 3ኛ ወገን በመሰጠቱ ምክንያት ስለሆነ በአንቀፅ 39(1)(ሸ) መሰረት የስራ ስንብት ክፍያ ይገባል በማለት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም ስለዚህ የስር የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም ተብሎ እንዲፀና የሚል ነው፡፡ አመልካቾች የመልስ መልሳቸውን በ 18/12/2015 ኢ.ም በተፃፈ 03 ገፅ የሰበር ቅሬታቸውን በማጠናከር አቅርበው ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ በተገለፀው መሰረት የተጠቃለለ ስለሆነ እኛም ካስቀረብነው ጭብጥ አንፃር የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ እና የግራ ቀኙ ክርክር አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ተጠሪ ለአመልካች የስራ ስንብት ክፍያ ሊከፍላቸው ይገባል ወይስ አይገባም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ መርምረን እንደተረዳነው ከሆነ የአመልካቾች ዳኝነት ጥያቄ ተጠሪ ያለፍላጎታቸው በኤጀንሲ ተደራጁ በማለት ከአሰሪና ሰራተኛ ህግ ውጪ ያለማስጠንቀቂያ የስራ ውል በማቋረጥ ከስራ ያሰናበተን በመሆኑ የስራ ውሉ የተቋረጠው በህገወጥ በመሆኑ የስራ ስንብት ክፍያና የስድስት ወር ደመወዝ ካሳ እንዲከፍል የሚል ነው፡፡ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስ የስራ ውሉ የተቋረጠው በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀፅ 28(3)(ሐ) መሰረት የአገልግሎት አሰጣጥ ተደራሽ ለማድረግ የእውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር በማድረግ የአገልግሎት አሰጣጥን ለማሳለጥ እና ለማዘመን፣ የአሰራር ክህሎትንና የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ለማሳደግ የተቋሙን የአስተዳደር ጫና ለመቀነስ ሲባል የስራ ዘርፎችን አውት ሶርስ በማድረግ በ 3ኛ ወገን በውል ለማሰራት በማሰቡ ለሶስተኛ ወገን በመሰጠቱ የከሳሾች የስራ ውል የተቋረጠው በአግባቡ ስለሆነ የስራ ስንብት ክፍያም ሆነ የደመወዝ ካሳ ለመክፈል ህጉ አያስገድድም በማለት ተከራክሯል፡፡ በእርግጥ የስራ ቅጥር ውል ህጋዊ ወይም ህጋዊ ባልሆነ ምክንያቶች ሊቋረጥ ይችላል፡፡ የስራ ውል በህጋዊ መንገድ ተቋረጠ የሚባለው በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀፅ 24፣ 25፣ 27፣ 28፣ 29፣ 31 እና 32 መሰረት ነው፡፡ አሁን በያዝነው ጉዳይ በአመልካቾችና በተጠሪ መካከል ያለው የስራ ውል የተቋረጠው አመልካቾች የሚሰሩት የጥበቃና የፅዳት ስራ መደብ ተጠሪ ለሌላ 3ኛ ወገን አሳልፎ በመስጠቱ (አውት ሶርስ) ምክንያት ነው፡፡ በዚህ መሰረት የስራ ውል ከተቋረጠ የስራ ውል መቋረጡ ህጋዊ አሰራር እንደሆነ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀፅ 28(1)(መ) እና 28(3)(ሐ) ይደነግጋል፡፡ የስር ሁለቱም ፍርድ ቤቶች የስራ ውል የተቋረጠው በህጋዊ መንገድ እንደሆነ አረጋግጠዋል፡፡ አመልካቾችም የስራ ውል የተቋረጠው

በህጋዊ መንገድ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ ተቃውሞ የላቸውም፡፡ የአመልካቾች ክርክር የስራ ውሉ የተቋረጠው ህጋዊ ቢሆንም በድርጅት ውስጥ ረጅም ዘመን ያገለገሉ መሆናቸውንና የቤተሰብ አስተዳዳሪ በመሆናቸው በጉዳት ላይ ስለምንወድቅ የስራ ስንብት ክፍያ ሊከፈለን ይገባል የሚል ነው፡፡ የስራ ውሉ የተቋረጠው በህጉ አግባብ ነው ከተባለ የስራ ስንብት ክፍያ ተጠሪ ሊከፍል ይገባል ወይስ አይገባም የሚለው ጉዳይን በተመለከተ በእርግጥ የስራ ውሉ በህግ መሰረት ቢቋረጥም አሰሪው የስራ ስንብት እና ካሳ ክፍያ ሊከፍል እንደሚገባ በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ያስገድዳል፡፡ በሌላ በኩል የስራ ውሉ የተቋረጠው በህገወጥ መንገድ ከሆነ የስራ ስንብት ክፍያ አሰሪው ለሰራተኛው ለመክፈል የሚገደደው አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀፅ 39(1)(ለ) ድንጋጌ በግልፅ ያስረዳል፡፡ የስራ ውል ከህግ ውጭ ሲቋረጥ አሰሪው ካሳ ሊከፍል እንደሚገደድ አንቀፅ 43 ስር ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በሌላ በኩል የስራ ስንብት ክፍያና ካሳ አሰሪው ለሰራተኛው ሊከፍል የሚገባው በአንቀፅ 39(1)ከ (ሀ) እስከ (ቀ) ድረስ ተዘርዝሯል፡፡ አሁን በያዝነው ጉዳይ የአመልካቾች የስራ ውል የተቋረጠው ተጠሪው አመልካቾች ስራ መደብ ለሌላ 3ኛ ሰው በመስጠቱ አውት ሶርስ ምክንያት ነው፡፡ አሰሪው የስራ መደቡን ለሌላ 3ኛ ወገን ከሰጠ አውት ሶርስ ካደረገ በዚህ መሰረት የስራ ውሉ ከተቋረጠ አሰሪው የስራ ስንብት ክፍያ ሊከፍል እንደሚችል በአንቀፅ 39(1) ከ (ሀ) እስከ (ቀ) ስር በግልፅ አልተደነገገም፡፡ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ያለው የስራ ውል የተቋረጠው በአንቀፅ 28(1)(መ) እና 28(3)(ሐ) መሰረት በመሆኑ በዚህ ድንጋጌ መሰረት የስራ ውል ለተቋረጠበት ስራተኛ አሰሪው የስራ ስንብት ክፍያ እንደሚከፍል በአንቀፅ 39(1) ከ (ሀ) እስከ (ቀ) ስር ያልተገለፀ ስለሆነ አሰሪው ለሰራተኛው የስራ ስንብት ክፍያ የሚከፍልበት ምክንያት የለም፡፡ በህግ ውስጥ በግልፅ ያልተሸፈነ ጉዳይ በመሆኑ የስንብት ክፍያ እንዲከፍል መወሰኑ የህጉን አላማ ሊያሳካ አይችልም፡፡ ህግ አውጪው በግልፅ የተወውን ጉዳይ ትርጉም የምንሰጥበት በቂ ምክንያት የለም ዳኞች ህጉን መተርጎም የሚችሉት ህጉ ግልፅ ሳይሆን ለትርጉም የተጋለጠ በሆነ ጊዜ ብቻ ነው፡፡ ይህ ጉዳይ በህግ ውስጥ በግልፅ ያልተሸፈነ ሆኖ እያለ በትርጉም የምናቃናበት ምክንያት ሊኖር አይችልም፡፡ በሌላ በኩል የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሚሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም በማናቸውም ፍርድ ቤቶች አስገዳጅነት እንዳለው ተደንግጎ እያለ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አስገዳጅ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ውሳኔን በሚቃረን መንገድ በህግ ውስጥ በግልፅ ያልተሸፈነ ጉዳይ ትርጉም በመስጠት የአዋጁን አንቀፅ 39(1)(ሸ) በመጥቀስ ተጠሪ የስራ ስንብት ክፍያ ሊከፍል ይገባል ሲል መወሰኑ ስህተት ነው፡፡ ይህንን ስህተት በይግባኝ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሻር የስራ ስንብት ክፍያ ተጠሪ ለአመልካቾች ሊከፍል አይገባም በማለት መወሰኑ

የሚነቀፍ አይደለም፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከዚህ ጉዳይ ጋር በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ በሰበር መዝገብ ቁጥር 22275 በቅፅ 6 ላይ የስራ ውል የተቋረጠው በህግ አግባብ በመሆኑ የስንብት ክፍያም ሆነ የደመወዝ ካሳ አሰሪው ሊከፍል አይገባም በማለት አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ስንብቱ ህጋዊ ከሆነ የደመወዝ ካሳ ሊከፍል እንደማይገባ በሰበር መዝገብ ቁጥር 38435 አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በሌላ በኩል በሰራተኛው ጥፋት የስራ ውል ከተቋረጠ የስራ ስንብት ክፍያም ሆነ ካሳ ሊከፍል እንደማይገባ በሰበር መዝገብ ቁጥር 69125 በቅፅ 13 ላይ ትርጉም ተሰጥቷል፡፡

ሲጠቃለል በአመልካቾችና በተጠሪ መካከል ያለው የስራ ውል የተቋረጠው አመልካቾች የተቀጠሩበት የጥበቃና የፅዳት ስራ መደብ ለሌላ ሶስተኛ ወገን ተጠሪ አሳልፎ በመስጠቱ (አውት ሶርስ) በአዋጁ አንቀፅ 28(3)(ሐ) መሰረት በመሆኑ በዚህ መሰረት የስራ ውል ከተቋረጠ የስራ ስንብት ክፍያ መክፈል እንደሚገባ በአዋጁ አንቀፅ 39(1) ከ (ሀ) እስከ (ቀ) ድረስ ያልተዘረዘረ በመሆኑ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለአመልካቾች የስራ ስንብት ክፍያ ሊከፍል አይገባም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 22275 ላይ ከሰጠው ውሳኔ ጋር ተመሳሳይ ውሳኔ በመሆኑ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት ባለመኖሩ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

ውሳኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 294246 በቀን 01/07/2015 ኢ.ም የሰጠው ፍርድ ከሰበር መዝገብ ቁጥር 22275፣ 39861፣ 69125 እና 38435 አንፃር እና ይህ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 248762 በቀን 30/09/2016 ኢ.ም ከሰጠው ፍርድ ጋር ተመሳሳይ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት ስለሆነ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስነ ስርአት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9(1)(ሀ) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠ እግድ ካለ ተነስቷል፡፡

ትዕዛዝ

- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 244553

ጥቅምት 4 ቀን 2017 ዓ.ም

**ዳኞች** ፡-ሸመክት አሰፋ

ገበየሁ ፈለቀ

አለማየሁ ሹናራ

ተናኜ ጥላሁን

ዘውዲቱ ታደሰ

አመልካች፡- የአ.ብ.ክ.መ ጤና ጥበቃ ቢሮ - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ነጋ ብርሀኑ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ - አልቀረቡም

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ሲሆን ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች መጋቢት 18 ቀን 2016 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው አቤቱታ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 01-54141 ግንቦት 12 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 237588 የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረቡ መነሻነት ነው፡፡ ጉዳዩ ከግንባታ ውል መፍረስ ጋር ተያይዞ የተጠየቁ ክፍያዎችን የሚመለከት ክርክር ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በአ/ብ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት ነው፡፡ በአ/ብ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር አመልካች ከሳሽ እንዲሁም ተጠሪ እና በዚህ የሰበር ክርክር ተካፋይ ያልሆኑ ቡና ኢንተርናሽናል ባንክ እና ንብ ኢንሹራንስ ተከሳሾች ነበሩ፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አመልካች የካቲት 10 ቀን 2012 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት ክስ ይዘት ከተጠሪ ጋር በ06/08/2007 ዓ.ም በተደረገ የግንባታ ውል  በደቡብ ወሎ ዞን ቦረና ወረዳ የበታ ጤና ጣቢያ ግንባታ እንዲያከናውን በብር 3,878,504.40 (ሶስት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሰባ ስምንት ሺህ አምስት መቶ አራት ብር ከአርባ ሳንቲም) አመልካች ለመክፈል ተስማምቼ የግንባታ ርክክብ በቀን 06/09/2007 ዓ.ም ሊሆን ተስማምቶ፣  በውሉ መሰረት ግንባታውን ሊያከናውን ስላልቻለ በቀን 06/08/2008 ዓ.ም የግንባታ ውሉ ተቋርጧል፡፡ ቀሪውን ስራ ለቸቸላ ኢንጅነሪንግ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ የተዋዋልኩትን ብር 4,509,473.81 (አራት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ አራት መቶ ሰባ ሶስት ብር ከሰማንያ አንድ ሳንቲም) እና የመዘግየት ቅጣት ተጠሪ እንዲከፍል፣ የቅድመ ክፍያ ብር 1,163,551.32 (አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ስልሳ ሶስት ሺህ አምስት መቶ ሃምሳ አንድ ብር ከሰላሳ ሁለት ሳንቲም) ያልመለሰ ስለሆነ ከ2ኛ ተከሳሽ (ቡና ኢንተርናሽናል) ጋር እንዲከፈል፣ የመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትናውን ብር 387,850.44 (ሶስት መቶ ሰማንያ ሰባት ሺህ ስምንት መቶ ሃምሳ ብር ከአርባ አራት ሳንቲም) ከ3ኛ ተከሳሽ (ንብ ኢንሹራንስ) ጋር ክርክሩ ካስከተለው ወጪና ኪሳራ ጋር እንዲፍሉኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

ተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

ፍሬ ጉዳዩን በማስረጃ የማጣራትና የመመዘን ስልጣን ያለው የስር ፍ/ቤት የአመልካችን እና በዚህ መዝገብ ተካፋይ ያልሆኑንት 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች የጽሁፍና የቃል ክርክር ሰምቶ ያቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ በብይን ውድቅ ካደረገ በኋላ፣ በፍሬ ጉዳይ ላይ እልባት ለመስጠት ተገቢነት ያላቸውን ጭብጦች ለይቶ በመያዝ በግራቀኙ የቀረቡትን የሰነድ ማስረጃዎች ከመረመረ በኂላ በአመልካችና ተጠሪ መካከል በተደረገው የግንባታ ውል መቋረጥ ጥፋቱ የተጠሪ ስለሆነ ተጠሪ የሰራው ስራ ብር 434,473.65 (አራት መቶ ሰላሳ አራት ሺህ አራት መቶ ሰባ ሶስት ብር ከስድሳ አምስት ሳንቲም)  ያልተከፈለው በመሆኑ ይህ ገንዘብ ተጠሪ ለአመልካች ሊከፍለው ከሚገባው ገንዘብ በመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትና ውሉ ከተመለከተው ገንዘብ ብር 387,850.44 (ሶስት መቶ ሰማንያ ሰባት ሺህ ስምንት መቶ ሀምሳ ብር ከ 44/100) እና ለተጠሪ ከተከፈለው ቅድመ ክፍያን በተመለከተም ለአመልካች ስለመመለሱ ተጠሪ ቀርቦ ያልተከራከረ ስለሆነ  ቅድመ ክፍያ ብር 1,163,551.32/ አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ስድሳ ሦስት  ሺ አምስት መቶ አምሳ አንድ ብር ከሰላሳ ሁለት ሳንቲም/ ተጠሪው ለአመልካች ሊመልስ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪው የሠራው ሥራ በአመልካች በኩል በቀረበ ማስረጀ እንደተረጋገጠው ብር 434,473.65/ አራት መቶ ሰላሳ አራት ሺ አራት መቶ ሰባ ሶስት ብር ከስድሳ አምስት ሳንቲም/ ስለሆነ፣ በግንባታ ውሉ አንቀጽ 5.4 መሠረት ተጠሪው ከተከፈለው የቅድመ ክፍያ ገንዘብ ላይ ይህ ገንዘብ ተቀናሽ ሲደረግ የሚቀረውን ብር 729,077.67/ ሰባት መቶ ሃያ ዘጠኝ ሺህ ሰባ ሰባት ብር ከስድሳ ሰባት ሳንቲም/ ተጠሪው ለአመልካች ሊከፍል ይገባል በማለት እንዲሁም የመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትና ብር 378,850.44/ ሦስት መቶ ሰባ ስምንት ሺ ስምንት መቶ አምሳ ብር ከአርባ አራት ሳንቲም/ ለተጠሪው  ሊከፍል ከሚገባው ተቀናሽ በማድረግ የተጠሪ ኃላፊነት ብር 1,116,928.11 (አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ አስራ ስድስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሀያ ስምንት ብር ከ 11/100) በመሆኑ ተጠሪ ይህን ገንዘብ እስከ ወለዱ ሊከፍል ይገባል፡፡  በአመልካችና በተጠሪ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

መካከል የተደረገው የግንባታ ውል ስራው ሳይጠናቀቅ የተቋረጠ በመሆኑ ሊከፈል የሚችል የመዘግየት ቅጣት የለም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች የህንን ውሳኔ በመቃወም ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የይግባኝ አቤቱታውን ያቀረበ ቢሆንም ውሳኔው ሳይለወጥ ቀርቷል፡፡

አመልካች መጋቢት 18 ቀን 2016 ዓ.ም ጽፎ ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ይህን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ሲሆን ይዘቱም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 73437 እና በሰ/መ/ቁ 95405 እንዲሁም በሰ/መ/ቁ 158350 እና በመ/ቁ 69797 የመዘግየት ቅጣት እና የጉዳት ካሳ ከመልካም ስራ አፈጻጸም ጋር ያለውን ቁርኝት በተመለከተ ሁለት የሚጋጭ ውሳኔ በመስጠቱ ምክንያት ለክርክር መነሻ በመሆናቸው የይግባኝ ቅሬታ እና የሰበር ቅሬታ የተጠየቀባቸው መዝገቦች ከ60 በላይ በመሆናቸው በችሎቱ ላይም ሆነ በአቃቢ ህግ ላይ የስራ ጫና እና በመንግስት ላይ ከፍተኛ ወጪ እያስከተለ ስለሚገኝ የሚጋጩትን ውሳኔዎች ሰበር ሰሚ ችሎቱ በሰባት ዳኛ ትርጉም በመስጠት እንዲያስታርቃቸው እንጠይቃለን፡፡ ተጠሪ በስምንት ወር ውስጥ ስራውን ሰርቶ ህብረተሰቡ አገልግሎት እንዳያገኝ ማድረግ ነበረበት ነገር ግን ይህን ማድረግ ባለመቻሉ ግንባታው ከመዘግየቱም በላይ ህብረተሰቡ ማግኘት የነበረበትን የመጠጥ ውሀ አገልግሎት በማዘግየቱ በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰ/መ/ቁ 95405 እና 73437 የተሰጡት ውሳኔዎች ህጉን መሰረት ያደረጉ በመሆኑ ሊጸኑና ተጠሪ የመዘግየት ቅጣት ሊከፍል ይገባል፡፡

የፍ/ህ/ቁ 1889 መቀጮን በሚመለከት የሚደነግግ እንጂ የጉዳት ኪሳራን የሚመለከት ድንጋጌ ባለመሆኑ የሰበር መ/ 158350 እና 69797 ከመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትና በላይ የደረሰ ጉዳት ሊካስ አይገባም በማለት ይህንን ድንጋጌ በመጥቀስ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡ በሰ/መ/ቁ 95405 እና 73437 ላይ በተሰጡት ውሳኔዎች በፍ/ህ/ቁ 3291(2) ፣ 1790 (2) ፣ 2090 (1) እና 2091 ን መሰረት በማድረግ ከመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትናው መጠን በላይ የደረሰ ጉዳት ኪሳራ ሙሉ ለሙሉ ተቋራጮች ሊከፍሉ ይገባል በሚል ህጉን በአግባቡ በመተርጎም የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ በሰ/መ/ቁ 69797 ስር የጉዳት ኪሳራ ከመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትና በላይ ሊከፈል አይገባም በማለት የተሰጠው ውሳኔ ተሽሮ በሰ/መ/ 95405 እና 73437 ላይ የደረሰ ጉዳት ከመልካም ስራ አፈጻጸም በላይ ቢሆንም ሊከፈል ይገባል በማለት የተሰጠው ውሳኔ እንዲጸና፣ ተጠሪ የመዘግየት ቅጣት በፍ/ህ/ቁ 1889 መሰረት 387,580.44 (ሶስት መቶ ሰማንያ ሰባት ሺህ አምስት መቶ ሰማንያ ብር ከ 44/100) ሊከፍል ይገባል፡፡ ውሉ ሲቋረጥ አመልካች ያልተሰራውን ስራ በሌላ ተቋራጩጭ በማሰራት 4,509,473.81 (አራት ሚሊዮን አምስት መቶ ዘጠኝ ሺህ አራት መቶ ሰባ ሶስት ብር ከ 81/100) ጉዳት ደርሶብናል፡፡ በስር ፍ/ቤቶች የመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትናውን 387,580.44 (ሶስት መቶ ሰማንያ ሰባት ሺህ አምስት መቶ ሰማንያ ብር ከ 44/100) ይክፈል ስለተባለ ይህ ተቀንሶ ከመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትናው በላይ ለደረሰው ጉዳት በፍ/ህ/ቁ 3291(2) ፣ 1790 (2) ፣ 2090 (1) እና 2091 መሰረት 677,592.62 (ስድስት መቶ ሰባ ሰባት ሺህ አምስት መቶ ዘጠና ሁለት ብር ከ 62/100) ተጠሪ ሊከፍል ይገባል ተብሎ ይወሰንልን በማለት ጠይቋል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች ከተጠሪ ጋር ባደረገው ውል ላይ ተጠሪ የመዘግየት ቅጣት እንዲከፍል የተዋዋለ መሆኑ በተገለጸው ሁኔታ ተጠሪ በውሉ የተወሰነውን የመልካም አፈጻጸም ገንዘብ ብቻ እንዲከፍል የተወሰነበት አግባብ በፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 158350 በሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ መሰረት የመዘግየት ቅጣት ሊከፍል አይገባም ተብሎ መወሰኑ፤ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 95405 ከሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ አንጻር እና ሌሎች ተያያዥ ነጥቦችን ከመመርመር አንጻር ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዟል፡፡

ተጠሪው ባለመገኘቱ እና በአዲስ ዘመን ጋዜጣ በወጣ ማስታወቂያ በተደረገለት ጥሪ ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ታዟል፡፡

በሥር ፍርድ ቤቶች የተደረገው የግራቀኙ ክርክርና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር የሥር ክርክር፣ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ህጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ የቻልነው ፍሬ ጉዳዩን በማስረጃ የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት ተገቢነት ያላቸውን ጭብጦች ለይቶ ከያዘ በኂላ በግራቀኙ የቀረቡትን የሰነድ ማስረጃዎች መርምሮ አመልካቹ ዳኝነት ከጠየቀባቸው ውስጥ ተጠሪው ለአመልካች ሊከፍል ይገባዋል ያለውን ከላይ በተገለጸው የሥር ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ላይ የተመለከተውን ገንዘብ ተጠሪው እንዲከፍል ወስኖ፤ በሌላ በኩል የመዘግየት ቅጣትን በተመለከተ ተጠሪው ሊከፍል አይገባም ብሎ መወሰኑ በአመልካች ለቀረበው የሰበር ቅሬታ ምክንያት ሲሆን፣ ጉዳዩ ለሰበር ሊቀርብ ይገባል የተባለበት የማስቀረቢያ ነጥብም ይኸው ነጥብ ነው፡፡ ከዚሁ ነጥብ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከት፣ የሥር ፍርድ ቤት አመልካቹ የመዘግየት ክፍያን አስምልክቶ ያቀረበውን የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ ያደረገበት ምክንያት በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው የግንባታ ውል ስራው ሳይጠናቀቅ የተቋረጠ ስለሆነ፣ ባልተጠናቀቀ ግንባታ ሊከፈል የሚችል የመዘግየት ቅጣት የለም የሚል ድምዳሜ ላይ በመድረሱ ሲሆን የፍርድ ቤቱን ድምዳሜ አግባብነትን ስናይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ. 95405 እንዲሁም 158350 ላይ በሰጣቸው ውሳኔዎች ከመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትና ገንዘብ በላይ የሚወሰን የጉዳት ካሳ ሊኖር እንደማይችል አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠበት ሲሆን፣ በተያዘው ጉዳይ የግንባታ ውሉ የተቋረጠው በተጠሪው ጥፋት በመሆኑ ተጠሪው በውሉ መሠረት ሥረውን ላከናወነ እንደሆነ በተጠሪ ላይ ለሚደርስ ጉዳት አመልካቹ የመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትናውን ብር 387,850.44/ሦስት መቶ ሰማንያ ሰባት ሺ ስምንት መቶ አምሳ ብር ከአርባ አራት ሳንቲም/ እንደሚከፈለው በውሉ ላይ ተመልክቷል፡፡ በዚሁም ምክንያት ተጠሪው በውሉ መሠረት ሥራውን አጠናቀቆ ለአመላካች ሳያስረክበው በመቅረቱ በአመልካቹ ላይ ለደረሰው ጉዳት

ተጠሪው እንዲከፍል በሥር ፍርድ ቤት የተወሰነበት ሲሆን፣ አመልካቹ የመልካም ስራ አፈጻጸም እንዲከፈለው አመልካች ዳኝነት ጠይቆ እያለና ተጠሪው ይህንኑ የመልካም ዋስትና ብር 387,850.44/ሦስት መቶ ሰማንያ ሰባት ሺ ስምንት መቶ አምሳ ብር ከአርባ አራት ሳንቲም/ ተጠሪ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ለአመልካች እንዲከፍል የሥር ፍርድ ቤት እንደወሰነበት የሥር ውሳኔው ግልባጭ ላይ ተመልክቶ ያለ ሲሆን ይህ የሚያሳየው ተጠሪው በውሉ መሠረት የግንባታ ሥራውን ካልፈጸመ በአመልካቹ ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ሊከፈለው የሚገባው የካሳ መጠን ከመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና ገንዘብ መጠን ሊበልጥ እንደማይችል ነው፡፡

በዚሁ መሠረት ተጠሪው የግንባታ ሥራውን በውሉ መሠረት ሳያከናውን በመቅረቱ ምክንያት አመልካቹ ለደረሰበት ጉዳት ተጠቃሹ ገንዘብ እንዲከፈለው ተወስኖለት እያለ የመዘግየት ክፍያ እንዲከፈለው መጠየቁ የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ፣ የሥር ፍርድ ቤት ግንባታው ሳይጠናቀቅ ስለተቋረጠ ሊከፈል የሚችል የመዘግየት ቅጣት ክፍያ የለም በማለት የሰጠው ውሳኔ በውጤት ደረጃ ከላይ በተገለጸው ምክንያት የሚነቀፍ ባለመሆኑ ውሳኔው መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ነው ብለናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 237588 የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመት ባለመሆኑ ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 ፀንቷል ፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻቻሉ፡፡
3. መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ::

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

<u>ማሳታወሻ</u>፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁጥር---244577
ቀን- ጥቅምት 05 ቀን 2017 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ብርሃኑ አመነዉ
በዕዉቀት በላይ
ቀነዓ ቂጣታ
ብርሃኑ መንግስቱ
ማርታ ተካ

**አመልካቾች፡-** 1. አቶ ጠይብ ሰይዳን
2. አቶ ዓሊ ኡስማን — አልቀረቡም

**ተጠሪዎች፡-** 1. አቶ መሀድ አርቴ
2. አቶ አብዱ መሀመድ — አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ሁከት እንዲወገድ የቀረበ ክስን የተመለከተ ጉዳይ ሲሆን የተጀመረው በፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪዎች ከሳሾች ሲሆኑ አመልካቾች ደግሞ ተከሳሾች ነበሩ፡፡ የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ በፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 052-27-2014 ጥር 17 ቀን 2014 ዓ.ም ተሰጥቶ በየደረጃዉ ባሉት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና ሰበር ችሎት የጸናዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በሚል ነዉ፡፡

ተጠሪዎች በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- ተጠሪዎች የጋራ የሆነ በሀሮረይስ ወረዳ ለመደጋ ቀበሌ ዉስጥ የሚገኝ አዋሳኞቻቸዉ በክሱ ላይ የተገለጹ የእርሻ መሬቶች፣ የዉሃ ጉድጓዶች እና መስጊድ ባዶ መሬት ርዝመቱ 1,000 ሜትር በ705 ሜትር የሆነ የመሬት ይዞታዎች ያሉዋቸዉ ሲሆን ከአመልካቾች ይዞታና በተጠሪዎች ይዞታ መካከል ወደ ቶጎ ጫሌ የሚወስደዉ አስፋልት መንገድ ይገኛል፡፡ ከ2013 ዓ.ም የመጀመሪያ ወር ጀምሮ አመልካቾች በይዞታቸዉ ጣልቃ በመግባት ሁከት ፈጥረዋል፡፡ ስለሆነም አመልካቾች የፈጠሩት ሁከት እንዲወገድላቸዉ እንዲወሰን የሚጠይቅ ነዉ፡፡

አመልካቾች ለክሱ የሰጡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ጉዳይ መልስ ይዘት፡- የክስ አቤቱታው የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 244፣ 222፣ 223 እና የፍ/ህ/ቁ 1149 የሚፃረር በመሆኑ ተጠሪዎች በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33 መሰረት በአመልካቾች ላይ ክስ የመመስረት መብት የሌላቸው በመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 244(ረ) መሰረት ክሱ ዉድቅ ሊደረግ ይገባል፡፡ ተጠሪዎች ክስ የመሰረቱበት የመሬት ይዞታዎች የአመልካቾች ይዞታዎች ናቸው፡፡ በአመልካቾች እና በተጠሪዎች ይዞታዎች መካከል ወሰን አለ፡፡ ክርክር ያስነሳዉ መሬትም በአመልካቾች እጅና ይዞታ የሚገኝ ነው፡፡ የመሬት ይዞታዉ ስፋት 25 በ24 ሜትር ነው፡፡ መሬታችን የሚገኘው በሀሮረይስ ወረዳ ለመደጋ ቀበሌ ሲሆን የመሬቱ አጎራባችም ተጠቅሰዋል፡፡ አመልካቾች በተጠሪዎች ላይ ምንም አይነት የፈጠርነው ሁከት የለም፡፡ መሬቱም በእጃችን የሚገኝ እና እርሻም ታርሷል፤ የውሀ ጉድጓድ እና የመኖሪያ መንደራችንም በዚሁ መሬታችን ላይ የሚገኝ ነው በማለት ክሱ ዉድቅ እንዲደረግ በመጠየቅ ተከራክረዋል፡፡

የፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የቀረበውነ የመጀመሪያ መቃወሚያ ውድቅ አድርጎ በቦታው ድረስ በመሄድ በአካባቢው ያሉ ሰዎችን በመጠየቅ ማጣራት ካደረገ በኃላ ክርክር ያስነሳዉ የመሬት ይዞታ በተጠሪዎች እጅ የሚገኝ መሆኑን እና አመልካቾች ሁከት የፈጠሩ መሆኑን በማረጋገጥ ባለይዞታዎቹ ተጠሪዎች ናቸዉ በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝተዉ አመልካቾች ባቀረቡት ይግባኝ መነሻት ጉዳዩን የተመለከተዉ የሱማሌ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙን አከራክሮና መርምሮ ዉሳኔዉን በማጽናት ወስኗል፡፡ በመቀጠል አመልካቾች

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ያቀረቡ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘት፡- በስር ፍርድ ቤት የተነሳው ክርክር የሁከት ክርክር ሲሆን የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሁከት ተፈጥሯል አልተፈጠረም የሚለውን በምስክር ማረጋገጥ ሲገባው ምስክር ሳይሰማ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ የተጠሪዎች ወይም የስር ከሳሾች ነው በማለት ፍርድ መስጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል፡፡ ፍርድ ቤቶች በአንድ ጉዳይ ፍርድ ከመስጠታቸው በፊት የጉዳዩ አግባብነት ያላቸው ማስረጃዎች ሰምተዉ መሆን እንደሚገባዉ በሥነሥርዓት ህጉ በግልፅ የተቀመጠ መሆኑን እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ 42706 በቅፅ 08 በጉዳዩ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበት እያለ ፍ/ቤቱ የህንን የሥነ-ሥርዓት ህግ እና የሰበር ውሳኔ በማለፍ ማስረጃ ሳይሰማ ፍርድ መስጠቱ መሰረታዊ የማስረጃ የማሰማት መብት ያለፈ በመሆኑ ውሳኔው እንዲሻርላቸዉ የሚጠይቅ ነዉ፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ተጠሪዎች ባቀረቡት ክስ የጠየቁት ዳኝነት አመልካቾች በእርሻ ይዞታችን ላይ የፈጠሩት የሁከት ተግባር እንዲወገድልን የሚል በመሆኑ፤ የስር የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህንን ጉዳይ ሰምቶ ለመወሰን የሥረ-ነገር ስልጣን አለው መይስ የለውም? የሚለው ነጥብ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ. 229363 ከሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም ውሳኔ አንፃር ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በሰበር ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

ተጠሪዎች ለሰበር አቤቱታዉ የሰጡት መልስ ይዘት በአጭሩ፡- ለክሱ ምክንያት የሆነው ይዞታ አስቀድሞ የሁከት ተግባር ከመደረጉ በፊት በተጠሪዎች ወገን በእውነት የሚያዙበት መሆኑን በአግባቡ ማረጋገጥ ተገቢ እና እውነተኛ ፍትህ ለመስጠት አስፈላጊ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ዳኞች ቦታው ድረስ በአካል ተገኝተው ከአካባቢ መስተዳደር አባላት እና ከአካባቢ ሽማግሌዎች እና ነባር የሆኑ ሰዎች በማግኘት እና በማጣራት ለውሳኔያቸው መነሻ ማድረጋቸዉ የሚነቀፍበት ምክንያት የለም፡፡ ለስር ፍርድ ቤቶች የቀረበው ክስ ይህ ክስ በቀረበበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩ ለማየት እና መርምሮ ውሳኔ ለመስጠት የማያስችለው ህግ አለመደንገጉ እንዳለ ሆኖ ከሥር ፍርድ ቤት በቀረበው ክስ ላይ ለያዘው ጭብጥ የሰው ምስክሮች በማቅረብ ማጣራቱ እና መወሰኑም የሚነቀፍ እና መሰረታዊ የህግ ሥህተት ፈፅሟል የሚያስብል ነው በማለት በአመልካቾች መቅረቡ አግባብነት ካላቸው ህጎች ጋር ፈፅሞ የሚቃረን ስለሆነ አቤቱታው ውድቅ ሊሆንና የሥር ፍርድ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ቤት ውሳኔዎች ሊፀኑ ይገባል። ይህ የሚታለፍ ከሆነ እና የፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የማየት ስልጣን የለውም የሚባል ከሆነ ጉዳያችንን ለሚመለከተው ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ እንዲያሳርፍበት እንዲመለስ በመጠየቅ ተከራክረዋል። አመልካቾች ሰኔ 13 ቀን 2015 ዓ.ም የተዘጋጀ 1 ገጽ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸዉን በሚያጠናክር መልኩ አቅርበዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን እኛም አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል። የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር መርምረን እንደተረዳነዉ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሻዉ ጭብጥ፡- ተጠሪዎች ባቀረቡት ክስ የጠየቁት ዳኝነት አመልካቾች በእርሻ ይዞታችን ላይ የፈጠሩት የሁከት ተግባር እንዲወገድልን የሚል በመሆኑ፤ የስር የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህንን ጉዳይ ሰምቶ ለመወሰን የሥረ-ነገር ስልጣን ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ. 229363 ከሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም ውሳኔ አንፃር አለው ወይስ የለውም? የሚለው ነጥብ ነዉ።

ተጠሪዎች በፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ክርክር ባስነሳዉ የገጠር መሬት ይዞታቸዉ ላይ አመልካቾች ጣልቃ በመግባት ሁከት የፈጠሩባቸዉ ስለሆነ የሁከት ተግባሩ እንዲቆምላቸዉ ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ የሁከት ተግባሩ እንዲቆም ዉሳኔ ሰጥቶ በየደረጃዉ ባሉት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ችሎቶች ጸንቷል። ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለዉና አከራካሪዉ ነጥብ የፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ ጉዳዩን አከራክሮ ለመወሰን የሚያስችለዉ የስረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን አለዉ ወይስ የለዉም የሚለዉ ነዉ።

በመሠረቱ በሶማሌ ክልል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 152/2008 አንቀጽ 3(1) ግምት የሌለዉ በሚል በተመለከተዉ መሠረት የሁከት ይወገድልኝን ክስ ተመልክቶ የመወሰን የስረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን የክልሉ ወረዳ ፍ/ቤቶች ስልጣን ስር የሚወድቅ ሲሆን የዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ደግሞ ጉዳዩን በይግባኝ ተመልክቶ የመወሰን ስልጣን ይኖረዋል። ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ተመልክቶ የመወሰን ስልጣን የሌለዉ ፍ/ቤት ክስ ሲቀርብለት ወደ ክርክሩ ሂደት ከመግባቱ በፊት አስቀድሞ ጉዳዩን የማየት የስረ-ነገር ስልጣን ያለዉ መሆን አለመሆኑን መመርመር እንዳለበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 231(1/ለ) ተደንግጓል። ይህን አስመልክቶ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 244737 እና በሌሎች መዛግብት ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ተመልክቶ የመወሰን የስረ-ነገር ስልጣን የወረዳ ፍ/ቤት በሆነበት የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ተመልክቶ የሚሰጠዉ ዉሳኔ የሥረ-ነገር የዳኝነት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ስልጣን ሳይኖረዉ የሰጠዉ ስለሚሆን መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን በመግለጽ አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ተጠሪዎች በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ የገጠር መሬት ይዞታን አስመልክቶ የሁከት ይወገድልኝ የዳኝነት ጥያቄ በመሆኑ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ተመልክቶ የመወሰን ስልጣን የወረዳ ፍ/ቤት ሆኖ እያለ የፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን በቀጥታ ተቀብሎ ለማየት የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን ሳይኖረዉ አከራክሮ ዉሳኔ መስጠቱ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 244737 እና በሌሎች መዛግብት የሰጠዉን ትርጉም ያላገናዘበ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡ በየደረጃዉ ያሉት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ችሎቶች ይህንኑ ስህተት ማረም ሲገባቸዉ በፍሬ ጉዳዩ ላይ የተሰጠዉን ዉሳኔ በመመልከት ማጽናታቸዉ ተገቢ አይደለም፡፡

ሲጠቃለል ተጠሪዎች ያቀረቡትን የገጠር መሬት ይዞታን የተመለከተ የሁከት ይወገድልን የዳኝነት ጥያቄን ተመልክቶ የመወሰን የስረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን የወረዳ ፍ/ቤት ሆኖ እያለ የፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ ተቀብሎ አከራክሮ ዉሳኔ መስጠቱም ሆነ በዉሳኔዉ ላይ የቀረበዉን ቅሬታ ዉድቅ በማድረግ በየደረጃዉ ያሉት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ችሎቶች የሰጡት ዉሳኔ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 244737 እና በሌሎች መዛግብት የሰጠዉን ገዥ ትርጉም ያላገናዘበና በፌዴራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሸ) እና 10(1/ሐ) መሠረት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 052-27-2014 ጥር 17 ቀን 2014 ዓ.ም ተሰጥቶ በሶማሌ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 05-1-46/15 ታህሳስ 17 ቀን 2015 ዓ.ም በተሰጠ ዉሳኔ እና የክልሉ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 05-01-205/15 ጥር 30 ቀን 2015 ዓ.ም በሰጠዉ ትዕዛዝ የጸናዉ ዉሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1/ለ) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣኑ ተመልክቶ የመወሰን የስረ-ነገር ስልጣን የለዉም ተብሎ ተወስኗል
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
## የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መ/ቁ 244649

ጥቅምት 04 ቀን 2017 ዓ/ም

**ዳኞች:-** ሽመክት አሰፋ

ገበየሁ ፈለቀ

ዓለማየሁ ሹናራ

ተናኘ ጥላሁን

ዘዉዲቱ ታደሰ

አመልካች… ወ/ሮ እልፍነሽ ሴዲሶ - ቀረቡ

ተጠሪ… ወ/ሮ ክቤ ስዩም - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ከቤት ኪራይ ክፍያ ጋር ተያያዞ የቀረበ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ ወረዳ 9 ማህበራዊ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች በአሁን ተጠሪ ላይ ባቀረቡት የተሻሻለ የክስ አቤቱታ መነሻነት ነው።

የክሱ ይዘትም በአጭሩ:- አመልካች ለተጠሪ ከነሐሴ 21 ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ እስከ አሁን ቤቱን አከራይቻቸው ላለፉት አምስት አመታት የቤት ኪራይ እየከፈሉ ሲኖሩ ቆይተው አሁን ላይ ተጠሪ

በማላውቀው ምክንያት የ3 ወር የቤት ኪራይ ሳይከፍሉ የቆዩ በመሆኑ ያለባቸውን ያልተከፈለ ውዝፍ የቤት ኪራይ ብር 3,000 (ሶስት ሺህ ብር) እንዲከፍሉኝና ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

ተጠሪ ለቀረበባቸው ክስ ባቀረቡት መልስ አመልካች ክስ ባቀረቡበት ቤት ላይ መብትና ጥቅም የላቸውም የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማቅረብ በፍሬ ጉዳዩ ላይም በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ ወረዳ 9 የቤት ቁጥር 739 የሆነውን ቤት ከእናታቸውና አባታቸው በውርስ ያገኙት እነ ታምሩ ታደሰ (3 ወንድማማቾች) ለተጠሪ አከራይተውኝ የቤቱንም ኪራይ ለእነ ታምሩ ታደሰ ስከፍል የቆየሁና ያልከፈልኩት ውዝፍ የቤት ኪራይ ክፍያ የሌለ ሲሆን አመልካች በዚህ ቤት ውስጥ የገቡት እነ ታምሩ ታደሰ ካስጠጓቸዉ በኋላ አለቅም ብለው ክርክር ላይ እንዳሉ የሰማሁ በመሆኑ አመልካች ውዝፍ ኪራይ እንዲከፈላቸውም ሆነ ቤቱ እንዲለቀቅላቸው መጠየቅ አይችሉም ተብሎ ክሱ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልክ የቀረበለት ማህበራዊ ፍርድ ቤትም ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት ከአመልካች ተከራይተው መክፈል የሚገባቸውን የአምስት ወራት ክፍያ ባለመክፈላቸው ብር 5,000 (አምስት ሺህ) እንዲሁም ወጪና ኪሳራ ብር 250 (ሁለት መቶ ሃምሳ ብር) ሊከፍሉ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡

ተጠሪ ማህበራዊ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ቅሬታቸዉን በይግባኝ ለአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ማህበራዊ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት ባለቤት ናቸዉ የተባሉትን እነ አቶ ታምሩ ታደሰን (ወራሾችን) በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 40(2) መሠረት ወደ ክርክሩ እንዲገቡ በማድረግ አከራክሮ የመሰለውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ሲል ጉዳዩን ወደ ስር ማህበራዊ ፍርድ ቤት መልሶለታል፡፡

አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝተዉ ቅሬታቸዉን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳር ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው የከተማው ሰበር ችሎት ግራ ቀኙን አከራክሮ የአሁን አመልካች በስር ማህበራዊ ፍርድ ቤት የጠየቁት ዳኝነት ተጠሪ ያለባቸውን ያልተከፈለ ውዝፍ የቤት ኪራይ ብር 3,000 (ሶስት ሺህ) ኪራይ ይከፈለኝ ብቻ ሳይሆን ተጠሪ ቤቱን ለቀው እንዲያስረክቡ የሚል ጭምር በመሆኑ በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 50 መሰረት የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን አይደለም በማለት የሥር ማህበራዊ ፍርድ ቤት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ጉዳዩን ለማየት የሥረ-ነገር ስልጣን ሳይኖረው አይቶ የሰጠው ውሳኔ ስለሆነ መሰረታዊ የህግ ሥህተት የተፈፀመበት ነው በማለት የስር ማህበራዊ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ እና የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ውሳኔ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 348/1/መሰረት በመሻር ውሳኔ ሰጥቷል ፡፡

የሰበር አቤቱታውየቀረበዉ ይህንን ዉሳኔ በመቃወም ሲሆን ይዘቱም፡- አመልካች ለማኅበራዊ ፍርድ ቤት በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 91 መሠረት አሻሽዬ ያቀረብኩት ክስ ተጠሪ ያልከፈለችውን ውዝፍ የቤት ኪራይ ብር 3,000 /ሶስት ሺህ/ እንዲትከፍል የሚል ብቻ ነው፡፡ ተጠሪ ቤቱን እንዲትለቅ የሚል ዳኝነት አልተጠየቀም፡፡ በመሆኑም በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 50 መሰረት የስር ማህበራዊ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አከራክሮ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ስላለዉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በአመልካች ያልተጠየቀውን ዳኝነት እንደተጠየቀ በማድረግ የማኅበራዊ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለውም ሲል የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ መሻር የሚገባዉ ነው የሚል ነዉ፡፡

ይህ ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ተጠሪ ያልከፈሉኝ የቤት ኪራይ ብር 3000/ሶስት ሺህ/ እንዲከፍሉኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀው ባሉበት የስር የከተማ ሰበር ችሎት በሰጠው ውሳኔ አመልካች ባቀረቡት ክስ የቤት ይልቀቅልኝ የዳኝነት ጥያቄ ስላቀረቡ የስር ማህበራዊ ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ ለማየት ስልጣን የለውም ያለበትን አግባብነት አጣርቶ ለመመርመር ያስቀርባል ተብሎ ግራ ቀኑ ክርክር አድርገዉበታል፡፡

ተጠሪ ቀርበው በሰጡት መልስ በሥር አዲስ አበባ ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢ ነዉ የሚሉበትን ምክንያት በመዘርዘር እንዲጸናላቸዉ ጠይቀዋል፡፡

- የሰበር አመልካችም የሰበር አቤቱታቸዉን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርበዉ ክርክሩ ተጠቃሏል፡፡ የክርክሩ አመጣጥ እና ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን እኛም ቅሬታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ በስር ፍርድ ቤት ከተደረገዉ ክርክር የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እንዲሁም አግባብነት ካለዉ ህግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል ፡፡ እንደመረመርነዉም ቅሬታዉ ያስቀርባል ሲባል የተያዘዉ ጭብጥ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ተጠሪ ያልከፈሉኝ የቤት ኪራይ ብር 3000/ሶስት ሺህ/ እንዲከፍሉኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀው ባሉበት የስር የከተማ ሰበር ችሎት በሰጠው ውሳኔ አመልካች ባቀረቡት ክስ ስልጣን የለውም ያለበትን አግባብነት ለመመርመር በመሆኑ ከዚሁ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምረናል እንደመረመርነዉም የሰበር አመልካች ለስር ማህበራዊ ፍርድ ቤት ሰኔ 23 ቀን

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

2014 ዓ/ም በተጻፈ ያቀረቡት ክስ የሰበር ተጠሪ ያለባቸዉን ዉዝፍ የቤት ኪራይ ብር 3000 /ሶስት ሽህ ብር / እንዲከፍሉኝ ይወሰንልኝ የሚል ብቻ እንጅ ቤት ያስረክቡኝ የሚል ዳኝነት አለመጠየቃቸዉ በክሳቸዉ በግልጽ የተመለከተ ነዉ ፡፡በመሆኑም አመልካች ክሳቸዉን ለስር ማህበራዊ ፍርድ ቤት ማቅረባቸዉ የተሻሻለውን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 50 መሰረት ያደረገ እና ተገቢ የነበረ ነዉ ፡፡የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰበር አመልካች በክሳቸዉ አንስተዉ ዳኝነት ያልጠየቁበትን የቤት ይለቀቅልኝ ጉዳይ ዳኝነት ጠይቀዉበታል በሚል የማህበራዊ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የለዉም ማለቱ ክሱን በአግባቡ ያልተመለከተ እና የተጠየቀዉን ዳኝነት ያልተገነዘበ በመሆኑ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 182(2) ድንጋጌን እና የሚጥስ ስለሆነ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4) /ለ/ እና 10(1/ረ) መሰረት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ተብሎ ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ዉሳኔ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የስር ማህበራዊ ፍርድ ቤት እና ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የላቸዉም ሲል የሰጠዉ ዉሳኔ በሰበር አመልካች የተጠየቀዉን ዳኝነት ያላገናዘበ ስለሆነ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህት የተፈጸመበት ነዉ ተብሎ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የስር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የላቸዉም በማለት የዘጋዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ በፍሬ ጉዳዩ ተገቢ ነዉ የሚለዉን ዉሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 343(1) መሰረት መልሰናል፡፡

የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የሰ/መ/ቁ 244677

ጥቅምት 5 ቀን 2017 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሽመክት አሰፋ

ገበየሁ ፈለቀ

አለማየሁ ሹናራ

ተናኜ ጥላሁን

ዘውዲቱ ታደሰ

አመልካች፡- ወ/ሮ ሙሉነሽ ዳዕሞ- ተወካይ አቶ ዳሮታ ዳአሞ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አፍራስ አሳሮ - ቀረበ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ሲሆን ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች መጋቢት 20 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የዳውሮ ዞን የወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 21146 ግንቦት 16 ቀን 2014 ዓ.ም ፣ የክልሉ ከፍተኛው ፍርድ ቤት በመ/ቁ 16407 ነሐሴ 04 ቀን 2014 ዓ.ም እንዲሁም የደ/ም/ኢ/ህ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 18139 ታህሳስ 24 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጧቸው ፍርዶች ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመ በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ክሱ ተከሳሽ ያልከፈለውን ውዝፍ የቤት ኪራይ ከፍሎ ቤቱን ለቆ ያስረክበኝ በማለት በከሳሽ የቀረበ የዳኝነት ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የደ/ም/ኢ/ህ/ክ/መ/ የዳውሮ ዞን ወረዳ ፍ/ቤ ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አመልካች በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ የደ/ም/ኢ/ህ/ክ/መ/ የዳውሮ ዞን ሎሚ በሳ ወረዳ ጌንዳ ዋልጫ በሰሜን አቶ ደስታ ደርጩ በደቡብ አቶ ተሾመ አሎሎ ፣ በምስራቅ አቶ ኡቴ ሻንቆ በምዕራብ አቶ አባተ አስፋው የሚዋሰን ባለሁለት ደጃፍ ቆርቆሮ ቤት ተከሳሽ ከሟች ባለቤቴ በቃል ውል በወር 300 ብር ተከራይቶ ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ ሲከፍል ቆይቶ፣ ሟች ባለቤቴ አቶ ታይበላ ተሰማ ከሞተ በኋላ ከ2013 ዓ/ም መስከረም ወር ጀምሮ የቤቱን ኪራይ ክፍያ ስላቋረጠ ያልከፈለውን ውዝፍ ብር 5000/አምስት ሺህ ከፍሎ ቤቱን ለቆ እንዲያስረክበኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው።

ተጠሪ በሰጡት መልስ የቀረቡት ክርክር ይዘት ባጭሩ በሽያጭ ውል በብር 89,000 (ሰማንያ ዘጠኝ ሺህ) ብር ከቤቱ ባለቤት ለይ ገዝቼ፣ ከብር 100,000 (መቶ ሺህ) በላይ ወጪ በማድረግ ግንባታ በማድረግ ይገዤ ያለሁበት እንጂ በኪራይ የያዝኩት ይዞታ ስላልሆነ ልለቅ አይገባም በማለት ተከራክረዋል።

ጉዳዩ የቀረበለት ፍሬ ጉዳዩን በማስረጃ በማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው የስር ፍ/ቤት የግራቀችን የጽሁፍና የቃል ክርክር ከሰማና የቀረበለትን የሰነድ እና የሰው ማስረጃዎች ከክሱ ጋር በማገናዘብ ከመረመረው በኋላ የክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ/ቤት ተከሳሽ በኪራይ የያዘው ቤት ነው? ወይስ በግዢ ያገኘው ቤት ነው? የሚለውን ጭብጥ ለይቶ በመያዝ ቤቱን ተከሻሹ ከከሳሽዋ ባለቤት በወር በብር 300 ተከራይቶ መያዙን ያስረዱት የከሳሽ 3ኛ ምስክር ብቻ ናቸው በሚል እና፤ በአንጻሩ የከሳሽ 1ኛ ምስክርን ጨምሮ የተከሳሹ 6 ምስክሮችም ተከሳሹ ቤቱን ከከሳሽዋ ባለቤት በግዥ ያገኘው መሆኑን በመመስከራቸው ተከሳሹ ቤቱን በግዢ መያዛቸውን ፍርድ ቤቱ ለማረጋገጥ ችሏል የሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ ተከሳሽ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት/ይዞታ ተከሳሹ የያዘው በኪራይ ውል መነሻነት ሳይሆን በግዢ ነው በማለት ወስኗል።

አመልካች ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለደ/ም/ኢ/ህ/ክ/መ/የዳውሮ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲሁም ለደ/ም/ኢ/ህ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም ውሳኔው ሳይለወጥ ቀርቷል።

አመልካች መጋቢት 20 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ያቀረበው አቤቱታ ይህን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ሲሆን ይዘቱም ለስር ፍ/ቤት ተከሳሽ የቤት ኪራይ ውዝፍ ከፍሎ ቤቱን እንዲያስረክበኝ በሚል ክስ አቅርቤ ተከሳሽ ቤቱን ከባለቤቴ ገዝቻለሁ በሚል በእክል ሀዘን ላይ በነበርኩበት ጊዜ የሀሰት የቤት ግዢ ውል አዘጋጅተው ባልፈረምኩበት እና በሽያጭ ውሉ ላይም ባልተሳተፍኩበት ከፍ/ህ/ቁ 1723(1፣2) እና 1716 (1፣2) ተቃራኒ በሆነ መልኩ ግብይት ተፈጽሟል በሚል ከክርክሩ ጭብጥ በመውጣት ተከሳሽ ቤቱን የያዘው በኪራይ ውል ሳይሆን በግዢ ነው በማለት የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው።

በተከሳሽ በኩል የቀረቡት ምስክሮች የቤቱን ግማሽ ጎን በብር 90,000 (ዘጠና ሺህ)፣ ግማሹን በብር 45,000 (አርባ አምስት ሺህ) ለመግዛት ተስማምቶ ብር 25,000 (ሀያ አምስት ሺህ) በወቅቱ ሰጥቶ ብር 20,000 (ሀያ ሺህ) በ30/03/1912 ዓ/ም ለመስጠት ቃል መግባቱን ማስረዳታቸው ከቀረበው ሀሰተኛ ሰነድ ጋር የሚጣረስና ፍ/ቤቱም ተከሳሽ 1/4ኛ ክፍያ መፈጸሙን ሳይረጋገጥ መወሰኑ

እንዲሁም ተከሳሽ የቀበሌ አመራር በመሆኑ ሀሰተኛ ሰነድ አዘጋጅተው የሻጭ ባለቤት የግብይቱ አካል ሳትሆን ውልን ለማጽደቅ በህግ ስልጣን ወደ ተሰጠው አካል በወቅቱ አቅርበው ሳያስመዘግብ የሽያጭ ውል አለ ቢባል እንኳን የቋሚ ንብረት መዝገብ በእጄ ስለሚገኝ በህገወጥ ውል መብቴን የሚጎዳ ኢ-ፍትሀዊና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እንዲሻርልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የስር ፍ/ቤት ተጠሪ ውዝፍ ኪራይ ገንዘብ ከፍሎ ቤቱን ያስረክበኝ በማለት አመልካች ያቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄ ላይ ተንተርሶ አከራካሪውን ቤት ተጠሪ በግዢ ያገኘው ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ ግራቀኙ ካደረጉት ክርክርና አመልካች ካቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ አንጻር አግባብነት ያለው ስለመሆኑ ሊመረመር የሚገባ ሆኖ በመገኘቱ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪ ጥቅምት 27 ቀን 2015 ዓ.ም በተጻፈ የሰጡት መልስ ይዘት ባጭሩ ከአመልካች ጋር 10/06/2011 ዓ.ም ባደረግነው የመኖሪያ ቤትና አትክልቶች ሽያጭ ውል በአመልካች ስም ያለውን በሰሜን መንገድ፣ በደቡብ አብዮት አሰፋ፣ በምስራቅ ደስታ ደርጩ፣ በምዕራብ ኦሎሎ ኦምፔ የሚያዋስን ስፋቱ 8 ሜትር ርዝመቱ 19 ሜትር የሆነው 152 ካ.ሜ በብር 89,000 (ሰማንያ ዘጠኝ ሺህ) ከአመልካች ባል ላይ በእማኞች ፊት ገዝቻለሁ፡፡ ነባሩን ቤት አፍርሼ በብር 660,000 በሚገመት የሰራሁት ሲሆን ሚች ታይበላ ተሰማ ህጋዊ በሆነ መንገድ ሲያስተላልፍልኝ አመልካች አልተቃወመችም፡፡ ሰነዱ በሀሰት የተዘጋጀ ነው በሚል የቀረበው ክርክር በስር ፍ/ቤት ያልተነሳ ክርክር ነው፡፡ ውል ስለመኖሩ አመልካች ሳትክድ በውልና ማስረጃ ምዝገባ ክፍል አልተመዘገበም በሚል ብቻ ውሉ ህጋዊ አይደለም ለማለት እንደማይቻል የሰበር መ/ቁ 36887 ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት በግዢ ያገኘሁት ነው እንጂ ግማሹን ጎን ለመግዛት የተስማማሁበት ሰነድ የለም፡፡ በወቅቱ ከነበሩት 14 ምስክሮች ስድስቱ በስር ፍ/ቤት የቀረቡት ምስክሮችም ይህንኑ አስረድተዋል፡፡ አመልካች ለሚች ሁለተኛ ሚስቱ ስትሆን ከአመልካች ጋር የነበራቸው ጋብቻ በፍቺ ፈርሶ የራሷን ንብረት ወስዳ በራሷ ይዞታ ላይ እየኖረች ትገኛለች፡፡ ቤቱም የተፈራው ከአመልካች 1ኛ ሚስት ጋር እንጂ ከአመልካች ጋር አይደለም ሽያጩም የተፈጸመው የሚች የቀድሞ ሚስት ወ/ሮ ዘርፍነሽ ፈታ ከሞቱ በኋላ ነው፡፡ ቤቱ አለመመዝገቡ ውጤት የማይኖረው በፍ/ህ/ቁ 2877 በ3ኛ ወገኖች ዘንድ ነው፡፡ አመልካች ሚች ታይብላ ተሰማ ለተጠሪ ቤቱን ሲሸጥ ልትቃወም መብትና ጥቅም የሌላትና የላትም እንጂ፣ ቤቱ ይገባታል ቢባል እንኳን ሽያጩ እያወቀች በ6 ወር ውስጥ ወይም በማንኛውም ሁኔታ በሁለት አመት ውስጥ መቃወም እያለባት ከ 4(አራት ) አመት በኋላ ያቀረበችው ክስ ተቀባይነት የለውም፤ አከራካሪው ቤት ከሚች ታይብላ ተሰማ በህጋዊ መንገድ በግዢ አጊንቼ በስሜ አስመዝግቤ ገብር ገብሬ ማረጋገጫ ተሰጥቶኝ እየኖርኩ ያለሁበት መሆኑ ተረጋጦ የተወሰነ ውሳኔ በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶቹ ውሳኔ እንዲጸጸናልኝ እንዲሁም አመልካችዋ ወጪና ኪሳራ እንድትከፍለኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የግራቀኙ ክርክርና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፣ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ህጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ የቻልነው ፍሬ ጉዳዩን በማስረጃ የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ላለው የሥር ፍርድ ቤት በአሁን አመልካችዋ የቀረበለት የዳኝነት ጥያቄ፣  ተጠሪ ከሟች ባለቤቴ ጋር  ባደረጉት የቃል የከራይ ውል መሠረት በኪራይ የተረከበውን የክርክር ምክንያት የሆነውን ቤት ውዝፍ ኪራይ ከፍሎ፣ ቤቱን ያስረክበኝ የሚል የዳኝነት ጥያቄ ሲሆን፣ በተጠሪ በኩል በቤቱን የያዝኩት አመልካችዋ እንደሚሉት በኪራይ ሳይሆን፣ ከአመልካችዋ ባለበቤት ጋር ባደረኩት የግዥ ውል መሠረት ቤቱን ገዝቼው ነው በማለት ክደው በመከራከራቸው  ተጠሪው የቤቱን ኪራይ ሊከፍሉ ይገባል? ወይም አይገባም? ቤቱን ተጠሪው ለአመልካች ሊያስረክቡ ይገባል? ወይም አይገባም? ወደሚል ውሳኔ ለመድረስ ከመቻሉ በፊት ቤቱን ተጠሪ የተረከቡት በኪራይ ነው?  ወይስ በግዥ?  የሚለው ፍሬ ነገር በቅድሚያ መጣራት የሚገባው ከመሆኑ አንጻር፣ የሥር ፍርድ ቤቱ ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት የያዘው ጭብጥ አከራካሪውን ቤት ተከሳሽ የያዘው በኪራይ ነው ? ወይስ በግዢ ነው?  የሚለውን ጭብጥ  ከግራ ቀኙ ክርክር አንጻር ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት ተገቢነት ያለው ጭብጥ ቢሆንም ተጠሪው አከራካሪውን ቤት ያገኙሁት በግዢ ነው ቢሉም በተከሳሹ የቀረበውን ይህን መከራከሪያ አመልካችዋ በመካድ ተጠሪው ቤቱን የተረከቡት በግዢ ሳይሆን በኪራይ ነው በማለት ክርክር ከማቅረባቸው አንጻር ተጠሪው ቤቱን በግዢ ስለማግኘታቸው አግባብነት ያለውን ማስረጃ ማቅረብ የሚጠበቅባቸው ይሆናል፡፡ ሆኖም ተጠሪው በተገቢው የመንግስጥ አካል የተመዘገበ የቤት ሽያጭ ውል ካለማቅረባቸውም ሌላ፣ ለቤቱ ኪራይ ሲከፍሉ ስለመቆየታቸው ያቀረቡት መከራከሪያም ሆነ ማስረጃ አለመኖሩን ከሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ይዘት መረዳት ተችሏል፡፡

የማይንቀሳቀስ ንብረት ካለዉ ልዩ ባህርይ አንፃር ንብረቱን ከአንድ ወደ ሌላ ሰዉ በሽያጭ ለማስተላለፍ የሚደረግ ዉል በሦስተኛ ወገን ላይ ህጋዊ ዉጤት ያስከትል ዘንድ ዉሉ በህግ አግባብ በሚመለከተዉ አካል ዘንድ ካልተመዘገበ ውሉ ፈራሽ እንደሚሆንና የፍ/ሕ/ቁ አንቀጽ 2878 ን ዋቢ በማድረግ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 153664 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠበት ሲሆን በተያዘው ጉዳይም ተጠሪው ይህ አከራካሪ ቤት ከአመልካችዋ ባለቤት ላይ በግዢ ያገኙት መሆናቸውን ከመግለጽ በቀር፤ ቤቱን በግዢ ስለማግኘታቸውና በህግ አግባብ ባለው አካል ዘንድ የግዢና የሽያጭ ውሉ የተመዘገበበት የሰነድ ማስረጃ ተጠሪው በሥር ፍርድ ቤት ያላቀረቡ በመሆኑና የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነትን በሰው ምስክር ለማስረዳት የሚችሉበት የህግ መሠረት ባለመኖሩ አመልካቹ ቤቱን ገዝቼዋለሁ በማለት የሚያቀርቡት መከራከሪያ በአመልካችዋ ላይ ህጋዊ ውጤትን የሚያስከትል አይሆንም፡፡ በሌላ በኩል ግን ቤቱን ተጠሪው ከከሳሽዋ ባለቤት በወር በብር 300 ተከራይቶ መያዙን  የከሳሽ 3ኛ ምስክሮች ያስረዱ በመሆናቸው አመልካቹ ቤቱን

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በኪራይ ከተረከቡ መሆናቸውን መረዳት የሚቻል ሆኖ እያለ የሥር ፍርድ ቤት ተገቢነት በሌለው የማስረጃ ምዘና በደረሰበት ድምዳሜ ለቀረበለት የዳኝነት ጥያቄ ተገቢውን የዳኝነት ምላሽ ሳይሰጥ፣ በአመልካችዋ ባልተጠየቀ ዳኝነት ላይ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑና ተጠሪው በኪራይ ውል የተረከቡትን የክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት እና በቤቱ ኪራይ ሳይከፍሉ ለቆዩበት ጊዜ እንዲከፍሉ ተብሎ የቀረበባቸውን ውዝፍ የኪራይ ገንዘብ ብር 5000.00/አምስት ሺ.ህ/ በሚመለከት ስለመክፈላቸው ያቀረቡት ክርክርና ማስረጃ ባለመኖሩ የሥር ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ በቀረበው የዳኝነት ጥያቄ ላይ ውሳኔ ሳያሳርፍ መቅረቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው ብለናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ውሳኔ</u>

1. የደ/ም/ኢ/ህ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 18139 ታህሳስ 24 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪው በኪራይ ውል የተረከቡትን በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህ/ክ/መ/የዳውሮ ዞን ሊሚ በሳ ወረዳ ጌንዳ ዋልጫ በሰሜን አቶ ደስታ ደርጬ፣ በደቡብ አቶ ተሾመ አሎሎ፣ በምስራቅ አቶ ኡቴ ሻንቆ፣ በምዕራብ አቶ አባተ አስፋው የሚዋሰን ባለሁለት ደጃፍ ቆርቆሮ ቤት ዳኝነት የተጠየቀበትን የኪራይ ገንዘብ ብር 5000/አምስት ሺ.ህ/ ተጠሪው ለአመልካች በመክፈል ቤቱን ለአመልካች ያስረክቡ፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

<u>ማስታወሻ</u>፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የሰ/መ/ቁ :244816

8/2/2017

ዳኞች ሺመክት አሰፋ

ገበየሁ ፈለቀ

አለማየሁ ሹናራ

ተናኜ ጥላሁን

ዘውዲቱ ታደሰ

አመልካች፦ ወ/ሮ የሺወርቅ ውብነህ -አልቀረቡም

ተጠሪ፦ አቶ አወል መሃመድ - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በመራብ ጎጃም/ዞ/ከ/ፍ/ቤት ሆኖ አመልካች ተከሳሽ ሲሆኑ ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ እንዲሁም በዚህ ይግባኝ ክርክር ያልተጠሩት ቡና ኢንሹራንስ 1ኛ ጣልቃ ገብ ፤ቢያድግልኝ አማረ የተባለ ግለሰብ ደግሞ 2ኛ ጣልቃ ገብ የተደረጉ ሲሆን ሁለተኛው ጣልቃ ገብ ቢያድግልኝ አማረ ባለመቅረባቸው በሌሉበት ታይቶ ነው የተወሰነው፡፡ተጠሪ በቀን 2/6/2014 ዓ ም ያቀረቡት የካሳ ክስ ላይ የአመልካች በሆነ ሚኒባስ መኪና ቢያድግልኝ አማረ የተባለ ሾፌር እያሽከረከረው የተጠሪ በሆነው ባጃጅ ሰው አሳፍሬ እያወረድኩ ባለበት በአመልካች ምኒባስ ጥፋት ተገጭቼ በግራ

በኩል ታፋዬ እና በጣፊያዬ ላይ ጉዳት በመድረሱ እንዲሁም ባጃጁ ላይ ሙሉ ውድመት በመድረሱ በአጠቃላይ ብር 500,000 (አምስት መቶ ሺ ብር) ካሳ እንዲከፈለኝ በሚል አቤቱታ አቅርበው የነበረ ሲሆን አመልካች በሰጡት መልስ ምክንያታቸውን በዝርዝር በመግለጽ በተጠየቀው ልክ ካሳ ሊከፈል እንደማይገባ ተከራከሩ፡፡

የስር ፍ/ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ በተጠሪ ላይ ለደረሰ ጉዳት እና በባጃጁ ላይ ለደረሰ ጉዳት ጠቅላላ ድምር ብር 319,814.2 (ሶስት መቶ አስራ ዘጠኝ ሺ ስምንት መቶ አስራ አራት ከ 2 ሳንቲም) አመልካች እና 2ኛ ጣልቃ ገብ እንዲከፍሉ በማለት ወሰነ፡፡ከዚህ ገንዘብ ውስጥ

1ኛ ጣልቃ ገብ ቡና ኢንሹራንስ ብር 136,553 (አንድ መቶ ሰላሳ ስድስት ሺ አምስት መቶ አምሳ ሶስት) ብር እንዲከፍል ተወሰነ፡፡በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች ለአ/ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው የነበረ ሲሆን ፍ/ቤቱ የተጠሪ እድሜ 30 ተብሎ ተይዞ የተሰራውን የጉዳት ካሳ እድሜው 31 መሆኑን ከ 8ኛ ክፍል ካርድ አረጋግጫለሁ በማለት በቀሪው ዘመን የሚያጡት የ34 አመት ገቢ በመሆኑ በዚህ ነጥብ የተወሰነው ብር 79,426.2(ሰባ ዘጠኝ ሺ አራት መቶ ሃያ ስድስት ብር ከ2 ሳንቲም) ወደ ብር 77,156.88 (ሰባ ሰባት ሺ አንድ መቶ አምሳ ስድስት ብር ከ 88 ሳንቲም) በመቀነስ ሌላውን የውሳኔ ክፍል አጸናው፡፡የአ/ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የክልሉን ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔ አጸና፡፡

ይህ ፍ/ቤትም በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ የክልሉን የወንድ አማካይ እድሜ ግምት ውስጥ አስገብቶ ነው ወይስ አይደለም? እንዲሁም በስር ፍ/ቤት የባጃጁ ሙሉ ውድመት እንዲከፈል ከተወሰነ በሃላ የ1 አመት የተቋረጠ ገቢ እንዲከፍል የተወሰነው በህግ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን እንደጭብጥ በመያዝ ያስቀርባል በማለት የግራ ቀኙ መልስ እና የመልስ መልስ በማስቀረብ አከራክሮዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክር ይዘት አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም የቀረበውን ክርክር፣ ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ፣በዚህ መዝገብ ከተያዘው ጭብጥና ለጉዳዩ አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

በመጀመርያ አመልካች የተጠሪን እድሜ በተመለከተ የጡረታ እድሜ ላይ ተመስርቶ በ60 አመት ታስቦ ነው ካሳው ሊሰላ የሚገባው በማለት ያቀረቡትን መከራከርያና ፤በዚህ መዝገብም የክልሉ አማካኝ እድሜ ግምት ውስጥ ገብቶ ነወይ ካሳው የተሰላው ተብሎ የተያዘውን ጭብጥ በተመለከተ፤ የጡረታ እድሜ ሳይሆን መያዝ የሚገባው የወንድ አማካኝ የመኖር እድሜ ነው፡፡ጡረታ ከቅጥር ሰራተኛነት የሚወጣበት እንጂ የሀገራችን አማካኝ የመኖር እድሜ አደለም፡፡ በሌላ በኩል አማካኝ በህይወት የመኖር እድሜን አስመልክቶ ፍርድ ቤቱ ባገኘው ማስረጃ ላይ ተመስርቶ 65 አመት ነው በማለት ወስኗል፡፡ ይህ የሰበር ችሎትም ይህን በማለፍ የተለየ ማስረጃ ሰብስቦ መወሰን የሚገባው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለዚህ በዚህ ነጥብ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ አደለም፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የባጃጅ ሙሉ ውድመትና ተጠሪም ለደረሰባቸው የአካል ጉዳት በሚኖሩት እድሜ ልክ በፐርሰንት ተሰልቶ ይከፈል ተብሎ ከተወሰነ በኋላ በድጋሚ የተቋረጠ የአንድ አመት ገቢ ተብሎ መወሰኑ ተገቢ ነወይ? የሚለውን ተመልክተነዋል፡፡ በመሰረቱ ተጠሪ

ሆስፒታል ቆየሁ ያሉት ከወር ብዙም ላልዘለለ ግዜ ነው፡፡ለህክምና ፣ለአልሚ ምግብ እና ለአስታማሚ ወጪ ተብሎ የተወሰነላቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የጉዳት ካሳ በጉዳቱ መጠንና በሚኖሩት እድሜ ተሰልቶ ከተጎዱበት ግዜ ጀምሮ ተሰልቶ ተወስኖላቸዋል፡፡የባጃጁም ሙሉ ውድመት ክፍያም ተወስኖላቸዋል፡፡ ከዚህ ውጪ የአንድ አመት የተቋረጠ ጥቅም ተብሎ የተወሰነው አሳማኝ ምክንያት የሌለውና፤በፍ/ህ/ቁ 2090(1) ካሳ ከጉዳት ተመዛዛኝ መሆን ይገባዋል ከሚለውም ጋር የሚስማማ ሆኖ ስላላገኘነው ተገቢ አደለም ብለን ከዚህ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

- የአ/ብ/ክ/መ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 01-59533 በታህሳስ 14/2015 የወሰነውንና የዚሁ የአ/ብ/ክ/መ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ03-120874 በመጋቢት 8/2015ዓ.ም ያጸናውን ውሳኔ የአንድ አመት የተቋረጠ ጥቅም ለተጠሪ ብር

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

18911(አስራስምንት ሺ ዘጠኝ መቶ አስራአንድ) ይከፈል የተባለውን ብቻ ሽረን፤ሌላውን የውሳኔ ክፍል በማጽናት በፍ/ስ/ስ/ህግ/ቁ 348(1) መሰረት አሻሽለን ወስነናል፡፡

- በዚህ መዝገብ በግንቦት 18/2015 የተሰጠው እግድ ተነስቷል፡፡እግዱ ስለመነሳቱ እግድ ለደረሳቸው ክፍሎች ይጻፍ፡፡
- የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ ይቻቻሉ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ም

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መ/ቁ 245022

ጥቅምት 05 ቀን 2017 ዓ/ም

የዉዝፍ መዛግብት ሰበር ችሎት

**ዳኞች:-** ሽመክት አሰፋ

ገበየሁ ፈለቀ

ዓለማየሁ ሹናራ

ተናኘ ጥላሁን

ዘዉዲቱ ታደሰ

አመልካች ፡ አቶ እንግዳ የማነ አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡ 1ኛ ካራቆሬ ቅድስ አርሴማ ቤተክርስቲያን
2ኛ ኮ/ቀ ክ/ከተማ መሬት ል/ማኔ/ጽ/ቤት } **አልቀረቡም**

መርምረን ፍርድ ሰጥተናል

ፍርድ

ጉዳዩ የከተማ ይዞታ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን በስር ፍርድ ቤቶች አመልካች ከሳሽ የነበሩ ሲሆን ተጠሪዎች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በቀን 29/08/2013 ዓ.ም አሻሽለዉ ባቀረቡት የክስ አቤቱታ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር የመሬት አስተዳዳር ባለስልጣን የይዞታ ማርጋገጫ የምስክር ወረቀት በኮ/ቀ/ክ/ማ ወረዳ 04 የቤት ቁጥር አዲስ በነባር ይዞታነት ለድርጅት አገልግሎት የሆነ 32874 ካ/ሜ የተሰጠኝ ሲሆን 1ኛ መልስ ሰጪ በመስከረም 28/2011 ዓ.ም በሰሜን ምዕራብ በኩል በአመልካችና እና በ1ኛ ተጠሪ መካከል ያለዉን አጥር የቤትክርስቲያን ምዕመን አፍርሰዉ ከእኔ ግቢ ጋር ቀላቅለዉ ጥቅምት 1/2011 ደግሞ

ያፈረሱትን ይዞታ ወደ ቦታዉ እንዲመልሱ ከፓሊስ ሃይልና በወረዳ አስተዳዳር ጋር በመሆን ቢጠየቁም በአከባቢዉ ከፍተኛ ሁከት በመፍጠር አጥሩ ወደ ነበረበት ሳይመለስ ቀርቷል፡፡ በመሆኑም 1ኛ ተጠሪ ከይዞታዬ ቀንሰዉ የወሰዱትን 2300 ካ.ሜ ቦታ የ150 ዛፎች ግምት ብር1850 ፤እና የ200 ቆርቆሮ ግምት ብር 30000 እንዲከፍሉ እና ቦታዉን እንዲያስረክቡኝ ፤2ኛ ተጠሪ ለ1ኛ ተጠሪ የሰጠዉን የሊዝ ዉል እንዲሰርዝ ወይም ምትክ እና ካሳ እንዲሰጠኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት የሚጠይቅ ነዉ፡፡

1ኛ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት መልስ የዛፍና የቆርቆሮ ግምት ይከፈለኝ ሲሉ ያቀረቡት ክስ በተመለከተ ማን እንደወሰደዉ ባልተረጋገጠ ንብረት ላይ በደፈናዉ ያቀረቡት ክስ ስለሆነ ተቀባይነት የሌለዉ ነዉ ፡፡ የሊዝ ዉላችን ጸንቶ ባለበት ሁኔታ እና የሊዝ ዉል እንዲቋረጥ የተሰጠ አስተዳዳራዊ ዉሳኔ በሌለበት ሁኔታ መሬት ይለቀቅ በማለት ክስ መቅረቡም ያላግባብ ነዉ የሚል ይዘት ያለዉ ነዉ፡፡

2ኛ ተጠሪ በበኩሉ የእኔ ስራ የሊዝ ዉል አዋዉል ስባል የሊዝ ዉል ከማዋዋል የዘለለ በይዞታ ላይ መብት የመፍጠር ስልጣን የለኝም ፡፡ ይዞታዉ ከይገባኛል ነፃ ስለመሆኑ እና ከመመሪያዉ አኳያ ለአመልካቹ ይገባል ወይም አይገባም የሚለዉ እንዲሁም ከከተማዉ መዋቅራዊ ፕላን አኳያ ተጣርቶ የሊዝ ዉል እንዲፈቀድ እና መብት እንዲፈጠር የሚያደርገዉ እና በአዋጅ ስልጣን የተሰጠዉ ተቋም የይዞታ አስተዳዳር ነዉ እንጂ የመሬት ባንክና ማስተላለፍ ፅ/ቤት አይደለም፡፡ በመሆኑም በእኔ ላይ የቀረበዉ ክስ ያላግባብ ስለሆነ ዉደቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ክርክሩ በዚህ አግባብ የቀረበለት የስር ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ አከራካሪዉ የመሬት ይዞታ የሁለቱም ወገኖች ሳይሆን የመንግስት ይዞታ መሆኑ ስለተረጋገጠ የሊዝ ዉሉ እንዲሰረዝ ወይም ትክ ቦታ እንዲሰጠኝ የሚለዉ ክስ ዉድቅ ነዉ ፡፡የአጥር ቆርቆሮ እና የተቆረጠ ዛፍ በሚል ገምተዉ ከሳሽ ያቀረቡት የክፍያ ጥያቄም በአንደኛ ተጠሪ ትእዛዝ የፈረሰ አጥር ወይም የተቆረጠ ዛፍ መኖሩ ያልተረጋገጠ በመሆኑ ክሱ ዉደቅ ነዉ ሲል ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ቅሬታቸዉን በይግባኝ ለፌዴራል ለከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል ፡፡ ይግባኙ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን በማከራከር

ክርክር እና ማስረጃቸዉን መርምሮ የስር ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ ስህተት የለበትም በማለት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት አጽንቷል፡፡

የሰበር ቅሬታዉ የቀረበው በዚህ ላይ ሲሆን ይዘቱ በአጭሩ ፡- አመልካች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በስሜ ተመዝግቦ የተሰጠኝ ይዞታ እያለኝ ፤የአመልካች ይዞታ እና የ1ኛ ተጠሪ ይዞታ ጋር የምንዋሰን ሆነን ምንም ግንኙነት እንደሌለን በማድረግ የቀረበ ስለመሆኑና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ከተጠየቀው አስተያየት ውጪ በመስጠቱ እና የቢሮው ባለሙያ የሰጡት አስተያየት የስራቸው ተግባር ባልሆነ መልኩ አከራካሪ የተባለው ይዞታ የአመልካችም የ1ኛ ተጠሪም ይዞታ አይደለም የመንግስት ቦታ ነው በማለት በመግለጽ ከሙያቸው ውጪ የሰጡት ሙያዊ አስተያየት የማይመለከታቸውና የቢሮ ተግባር ያልሆነ መሆኑን ገልጸን ማስረጃም ከሚመለከተው የኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ የመሬት ባንክና ማስተላለፍ ጽ/ቤት እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ባንክና ማስተላለፍ ቢሮ ሙያዊ አስተያየት እንዲጠየቅልን የጠየቅን ቢሆንም ፤ አመልካችም የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ይዤ በተጨማሪም ይዞታዬ በ1988 ጂአይኤስ ካርታ ላይ በ1997 እና በ2003 የመስመር ካርታ ላይ ፍፁም ግልፅ በሆነ መንገድ ሙሉን የቦታ ስፋት ከነአቀማመጡ እየታየ ፤ በእጃችንም አድርገንም እየተገለገልንበት እያለን ምንም እንዳልያዝነው በማድረግ ማስረጃዎቹም ሳይታዩ በተጨማሪም 2ኛ ተጠሪ የኮልፌ ቀራኒዮ የመሬት ባንክና ማስተላለፍ ጽ/ቤት በማስረጃ ዝርዝሩ ላይ ባቀረበው የሰነድ ማስረጃ ላይ 1ኛ ተጠሪ ውል ሲዋዋል በቀን 19/08/2012 ዓ.ም በቁጥር ኮ/ቀ/ክ/ከ/የመ/ይ/አስ/ጽ/ቤት 3197/2012 በላከው ደብዳቤ ይዞታው መሬት ባንክ ያልገባ መሆኑንና በመንግስት እጅ ያልሆነ በመሆኑ ውል እንዲዋዋሉ ደብዳቤ ልኮ ሳለ፤ የኮ/ቀ/ክ/ከተማ የመሬት ባንክና ማስተላለፍ ጽ/ቤት ለካራቆሬ ቅድስት አርሴማ ቤ/ክርስቲያን ይዞታው መሬት ባንክ ያልገባ በመሆኑ 5112.68 ካ.ሜ እንዲካተት በቀን 19/08/2012 ዓ.ም በውል ቁጥር 39854 መሰረት ውል እንዲዋዋሉ አድርጎ በማስረጃ አስደግፎ ባቀረበበት ሁኔታ የስር ፍ/ቤቱ ከማይመለከተው አካል የቀረበ ነው ከማለት ውጪ ምላሹ  በገለልተኛ ወገን አልቀረበም በሚል አላስተባበሉም በማለት እንዲሁም አመልካች በሰነድ ማስረጃችን ሆነ በምስክሮች ስለ ተወሰደብን የቆርቆሮ አጥርም ሆነ ስለተቆረጠብን ዛፎች በ1ኛ ተጠሪ ትዕዛዝ ሰጪነት መሆኑን አስረድተን እያለ የተሰጡ ውሳኔዎች መሰረታዊ የማስረጃ ግድፈት እና የህግ ስህተት የተፈፀመባቸው በመሆኑ እንዲሻሩልን የሚል ይዘት ያለው አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

የሰበር ችሎቱም ክርክር ያስነሳው 2300 ካሬ ሜትር ይዞታ አመልካች በካርታ ከ/ቀ/የማ/ን/መ/11/23281/00 ሰኔ 02 ቀን 2000 ዓም የተሰጣቸው 32874 ካሬ ሜትር አካል ነው ወይስ አይደለም የሚለው በአግባቡ ባልተጣራበት እና ለጉዳዩ አወሳሰን የሚረዳ የጠራ ፍሬ ነገር በሌለበት ለ1ኛ ተጠሪ ልኬት የተሰራው በወቅቱ በመስክ ታጥሮ ያልተያዘ መሆኑ በተገለጸበት ሁኔታ የኮ/ቀ/ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ክርክር ያስነሳው ቦታ የሁለቱም ተከራካሪዎች ያልሆነ የመንግስት ይዞታ መሆኑን ገልጿል በሚል ብቻ ይዞታው የመንግስት መሆኑ ተረጋገጧል የሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ የአመልካችን ክስ የስር ፍ/ቤት ውድቅ የማድረጉን አግባብነት ከመሰረታዊ የጭብጥ አመሰራረት ከማስረጃ ምዘና መርህ ከፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁጥር 136፤137፤272፤327(3) 345 እና ከሌሎች ስለማስረጃ አቀራረብና አቀባባል ደንብ ከተደነገጉት ድንጋጌዎች ይዘትና ዓላማ እንዲሁም በሰ/መ/ቁ 72980 ከተሰጠው ገዥ ትርጉም አንጻር መርምሮ ለማጣራት ቅሬታዉ ሲባል ተብሎ ግራ ቀኙ ቀርበዉ ክርክር አድርገዉበታል፡፡

1ኛ ተጠሪ ቀርቦ የሰጠው መልስ ይዘት በአጭሩ ፡- የስር ፍርድ ቤት የክርክሩና የማስረጃ ምዘና ሂደት በጥንቃቄ እና ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ አመቺ በሆነ መልኩ መመርመሩን ፤ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ያስነሳው 2300 ካሬ ሜትር ቦታ የአሁን አመልካች ከተሰጣቸው 32874 ካሬ ሜትር አካል ነው ወይስ አይደለም የሚለው በአግባቡ ሳይጣራ በማለት የያዘው ጭብጥ ተደጋጋሚ ማረጋገጫ ሲልክ የነበረው የኮ/ቀ/ክ/ከተማ መሬት ልማት እና አስተዳደር ጽ/ቤት ደብዳቤዎች ተልከውለት እነሱን በማነፃፀር የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማት እና አስተዳደር ቢሮ በቀን 25/9/2014 ዓ/ም በሰጠው ምላሽ ላይ ለክርክር መሰረት የሆነው 2,300 ካሬ ሜትር ይዞታ የአመልካችም የ1ኛ ተጠሪም ይዞታ ያልሆነ የመንግስት ባዶ ቦታ መሆኑን አረጋግጦ ምላሽ መስጠቱን የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሰጠው ፍርድ ሀተታ ላይ በግልጽ ተቀምጦ እንዲሁም በማህደሩ ማስረጃው ተቀምጦ እያለ ሰበር ሰሚ ችሎቱ ለክርክር መሰረት የሆነው ይዞታ ለከሳሽ ከተሰጠው ይዞታ ጋር አካል ነው አይደለም በማለት ባልተጣራበት ሁኔታ በማለት ጭብጥ መያዙ አግባብ ስላልሆነ ይህ ጭብጥ ተነስቶ የስር ፍ/ቤትንም ሆነ የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲጸናልን፡፡ አመልካች በአቤቱታቸው ላይ 32.674 ካ/ሜትር ቦታ ተሰጥቶኝ እየተገለገልኩበት እገኛለሁ ይበሉ እንጂ የፌዴራል ፍ/ቤቶች ፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት አቶ የማነ ብርሃን ተገኝ የፍ/ባለእዳ በሆኑበት መዝገብ ላይ ይህ ይዞታ ለፍ/ባለመብቱ ከፊል ይዞታ በፍርድ የተካፈለ መሆኑን እና ቀሪ ይዞታው በአሁኑ ሰዓት

ይመለከተኛል የሚል አካል ቀርቦ ካርታ ሊያሰራለት እንዳልቻለ በእንጥልጥልም ላይ እንደሚገኝ የኮ/ቀ ክ/ከተማ መሬት ልማት አስተዳደር ጽ/ቤት በቀን 11/9/2014 ዓ/ም በተሰጠ ደብዳቤ አረጋግጦ እያለ የአሁን ከሳሽ ይህ ክርክር በይዞታው ላይ በሚደረግበት ሰዓት የፍ/ባለመብትን ይሁኑ ባለእዳ በግልጽ ባላሳዩበት ሁኔታ የፍ/ባለእዳ ናቸው ከተባለ ቀሪ ይዞታው በህጋዊ መልኩ የይዞታው ባለቤቶች ቀርበው ህጋዊ የሆነ ካርታ ያላሰሩ መሆኑን ይዞታውን የሚያስተዳድረው አካል በግልጽ ባረጋገጠበት ሁኔታ እና ክርክር የተነሳበት ይዞታ ከከሳሽ ይዞታ ጋር ፈጽሞ የማይገናኝ እና የመንግስትም ይዞታ መሆኑን በተረጋገጠበት ሁኔታ መዝገቡ ያስርቀባል ተብሎ ለክርክር መዳረጋችን አግባብ ስላልሆነ እንዲታረምልን የሚል ይዘት ያለው ክርክር አቅርቧል፡፡

2ኛ ተጠሪ ቀርቦ የሰጠው መልስ በአጭሩ፡- የአመልካች አቤቱታ በፍሬ ነገር የሚጣራና የማስረጃ ምዘና የሆነን ጉዳይ ችሎቱ ያስቀርባል ያለበት አግባብ ከአዋጁ አንቀፅ 10 (1) እና 2 (4) ድንጋጌ አንፃር ተገቢነት የለውም፡፡በስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክርክር በተነሳበት ጉዳይ ላይ በሰነድ እንዲሁም በሰው ማስረጃ ቦታው ድረስ ተወርዶ ጉዳዩ ተጣርቶ እና ምላሽ ቀርቦ እና ውሳኔ ሰጥቶ ሳለ ችሎቱ በስር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ የጠራ የፍሬ ነገር በሌለበት የተሰጠ ውሳኔ ነው በሚል የደረሰበት ድምዳሜ ተገቢነት የለውም፡፡አዋጅ ቁጥር 84/2006 አንቀፅ 26 የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ በከተማው አስተዳደር ወሰን ውስጥ ያለን የማይንቀሳቀስ ንብረት ይመዘግባል እንዲሁም ያስተዳደራል በሚል የሚደነግግ በመሆኑ ስልጣን ከተሰጠው ቢሮ ክርክር ያስነሳው ይዞታን በተመለከተ የቀረበን ምላሽ ፍ/ቤቱ ተቀብሎ ይዞታው የመንግስት ነው በሚል የደረሰበት ድምዳሜ ተገቢነት የለውም ስልጣን ሳይኖረው የቀረበ ምላሽ ነው በሚል የሚቀርብ መከራከሪያ ተገቢነት የሌለው በመሆኑ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እንዲሁም የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ እንዲያፀናልን በማለት ተከራክሯል፡፡

የሰበር አመልካችም የሰበር ቅሬታቸዉን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርበው ክርክሩ በዚሁ ተጠቃሏል፡፡ አጠቃላይ የክርክሩ አመጣጥ እና ይዘቱ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን እኛም ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ በስር ፍርድ ቤቶች ከተደረገዉ ክርክር የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እና ለጉዳዩ ተገቢነት ካለዉ ህግ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል ፡፡ እንደመረመርነዉም የሰበር ቅሬታዉ ያስቀርባል ሲበል የተያዘዉ ጭብጥ ክርክር ያስነሳው 2300 ካሬ ሜትር ይዞታ አመልካች በካርታ ኮ/ቀ/የማ/ን/መ/11/23281/00 ሰኔ 02 ቀን 2000 ዓም የተሰጣቸው 32874 ካሬ ሜትር አካል ነው ወይስ አይደለም የሚለው በአግባቡ ባልተጣራበት እና ለጉዳዩ አወሳሰን የሚረዳ የጠራ ፍሬ ነገር በሌለበት ለ1ኛ ተጠሪ ልኬት

የተሰራው በወቅቱ በመስክ ታጥሮ ያልተያዘ መሆኑ በተገለጸበት ሁኔታ የኮ/ቀ/ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ክርክር ያስነሳው ቦታ የሁለቱም ተከራካሪዎች ያልሆነ የመንግስት ይዞታ መሆኑን ገልጿል በሚል ብቻ ይዞታው የመንግስት መሆኑ ተረጋግጧል የሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ የአመልካችን ክስ የስር ፍ/ቤት ውድቅ የማድረጉን አግባብነት ከመሰረታዊ የጭብጥ አመሰራረት ከማስረጃ ምዘና መርህ ከፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁጥር 136፤137፤272፤327(3) 345 እና ከሌሎች ስለማስረጃ አቀራረብና አቀባባል ደንብ ከተደነገጉት ድንጋጌዎች ይዘትና ዓላማ እንዲሁም በሰ/መ/ቁ 72980 ከተሰጠው ገዥ ትርጉም አንጻር መርምሮ ለማጣራት መሆኑን ተገነዘበናል፡፡ በመስረቱ ክርክርን ለማስረዳት ማስረጃ የሚቀርብበት ሥርዓት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 223 መሠረት የሰው ማስረጃ ዝርዝር እና ተከራካሪዉ በዕጁ የሚገኝ የፅሁፍ ማስረጃን የሚቀርብበት ሲሆን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 145 መሰረት ደግሞ በተከራካሪ ዕጅ የሌሉ ወይም ለማቅረብ ከፍተኛ ወጭ የሚጠይቁ ማስረጃዎች በፍርድ ቤት እገዛ የሚቀርቡበት ነው፡፡ የሠነድ ማስረጃ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 137 መሠረት ክሱ እስከሚሰማበት ጊዜ ድረስ ማቅረብ የሚቻል ሲሆን በእነዚህ ሂደቶች ማስረጃው ያልቀረበው ተከራካሪው ባለማወቁ ወይም አዲስ የተገኘ ማስረጃ ከሆነ ደግሞ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 256 አግባብ ማስረጃው እንዲቀርብ ለፍርድ ቤት ጥያቄ ሊቀርብ እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ በዚህ አግባብ ማስረጃ እንዲቀርብ የሚጠየቀው ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ሲሆን ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በይግባኝ ደረጃ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 327(3) እና 345 መሠረት በልዩ ሁኔታ ማስረጃ የሚስተናገድበት ሥርዓትም ተዘርግቷል፡፡ በሌላ በኩል አንድ ፍርድ ቤት ለጉዳዩ አወሳሰን የጠራ ፍሬ ነገር የሌለ መሆኑን ከተገነዘበ ይኸው ፍሬ ነገር እንዲጣራ ተገቢ ነው ያለውን ማጣራት ሁሉ ማድረግ እንደሚችል የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 136፣137፣ 272፣ 327(3)፣ 345 እና ከሌሎች ስለማስረጃ አቀራረብና አቀባበል ደንብ ከተደነገጉት ድንጋጌዎች ይዘትና ዓላማ እንዲሁም ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 72980 ከሰጠዉ ገዥ ዉሳኔ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በያዝነዉ ጉዳይ ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰበር ቅሬታ የቀረበበትን ዉሳኔ የሰጠዉ ስለጉዳዩ የኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ መሬት ልማት እና አስተዳደር ጽ/ቤት የሰበር አመልካች ይዞታ ማረጋገጫ በተሰጣቸዉ ቦታ ላይ ፌዴራል ፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክሬት ቦታዉ ተካፍሎ በፍርድ ባለመብት እነ ፕሮፌሰር ክፍለ ስላሴ መያዙን ቀሪዉን ቦታ የፍርድ ባለዕዳዎች እነ የማነ ብርሃን ባለመቅረባቸዉ ያልወሰዱት መሆኑን በማረጋገጡ ፤የኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ አስተዳደርም አንደኛ የሰበር ተጠሪ በካርታ ከተሰጣቸዉ 1756 ካሬ ሜትር ዉጪ ያልተሰጣቸዉ እና በህጋዊ መንገድ ያልያዙ መሆኑን በማረጋገጡ፤እንዲሁም የኮልፌ መሬት ልማት እና አስተዳደር ጽ/ቤት የሰጠዉን ምላሽ እና የኮልፌ ቀራኒዮ አስተዳደር ጽ/ቤት የሰጠዉን ምላሽ በሚመለከት የአዲስ አበባ መሬት ልማት አስተዳደር ሁለቱን አገናዝቦ ስለሁኔታዉ አጣርቶ እዉነታዉን እንዲልክ በታዘዘዉ መሰረት አጣርቶ ግራ ቀኑ የሚከራከሩበት መሬት የሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች ይዞታ ያልሆነ የመንግስት ይዞታ ነዉ ብሎ በማረጋገጡ የተሰጠ ዉሳኔ ሲሆን የአጥር ቆርቀሮዉን እና የባህር ግምቱም የሰበር አመልካች በአንደኛ ተጠሪ ትእዛዝ መፍረስና መወሰዱን አላረጋገጠም ተብሎ ዉድቅ የተደረገ ነዉ ፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቱ እዉታዉን ለማረጋገጥ በሰ/መ/ቁ 72980 በተሰጠዉ ገዥ ዉሳኔ አግባብ ተገቢዉን እርቀት ሄዶ ማጣራት አድርጓል ከሚባል ዉጭ ማጣራት አላደረገም ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ በሌላ በኩል የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉን ዉሳኔዎች በማረም ላይ የተገደበ ስለመሆኑ የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80 (3-ሀ) እንዲሁም

በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 4 እና 10 ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻል ነዉ፡፡በመሆኑም  የስር ፍርድ ቤቶች ማስረጃን መዝነዉ የደረሱበትን የፍሬ ነገር ድምዳሜ ሰበር ሰሚ ችሎት  በድጋሚ ሊመረምር የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ የስር ፍርድ ቤቶች በሰጡት ዉሳኔ ላይ በዚህ ሰበር ችሎት በተያዘዉ ጭብጥ አግባብ የፈጸሙት መሰረታዊ የሆነ የጭብጥ አመሰራረትም ይሁን የማስረጃ ምዘና መርህ ስህተት መፈጸማቸዉን የዉሳኔዉ ይዘት የሚያሳይ ባለመሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠዉ ዉሳኔ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም ፡፡

በመሆኑም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ዉሳኔ

በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 113468 ሰኔ 22 ቀን 2014 ዓ/ም ተሰጥቶ ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 295472 ግራ ቀኙን አከራክሮ ጥር 23 ቀን 2015 ዓ/ም ዋለዉ ችሎት ያጸናዉ ፍርድ መሰረታዊነ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም ተብሎ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ጸንቷል ፡፡

የሰበር ክርክሩ ያከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ/ጋ

የሰበር መ/ቁ 245059

ጥቅምት 05 ቀን 2017 ዓ/ም

ዳኞች:- ሽመክት አሰፋ

ገበየሁ ፈለቀ

ዓለማየሁ ሹናራ

ተናኘ ጥላሁን

ዘዉዲቱ ታደሰ

አመልካች፡- አቶ አንዱአለም ተሰማ ለጫ - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ወ/ሪት አብስራ አድሃኖም ገ/እግዚአብሄር - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ከኪራይ ክፍያ ጋር ተያያዞ የቀረበ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌደራል መጀመሪያ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካች ላይ ባቀረቡት የክስ አቤቱታ መነሻነት ነው፡፡

የክስ አቤቱታው ይዘት በአጭሩ ተጠሪ በ13/06/10 ዓ/ም መኖሪያ ቤት ይዞታቸውን ለአምስት አመት ለንግድ ስራ አላማ ለአመልካች ማከራየታቸውን ፤ የመጀመሪያውን አመት ኪራይ ውሉ ሲደረግ በቅድሚያ የከፈሉ ሲሆን የቀሪዎቹን 4 አመታት ኪራይ የየ6 ወሩን በቅድሚያ ሊከፍሉ ፤የተርን ኦቨር ታክስ በውሉ ዘመን ውስጥ የሚመጣውን የመብራትና የውሀ ፍጆታ ክፍያ ለመክፈል ተስማምተው በተከራዩት ይዞታ ውስጥ ተጨማሪ ክፍሎችን በራሳቸው ወጪ ሰርተው ሊጠቀሙና የኪራዩ ዘመን ሲያልቅ የሰሯቸውን ክፍሎች ያለምንም ክፍያ ለተጠሪ አስረክበው ለመውጣት መዋዋላቸውን ይሁን እንጂ አመልካች በውሉ መሰረት ከህዳር እስከ ሚያዝያ 2014 ዓ/ም ያለውን የ6 ወር ኪራይ ብር 270,000 በቅድሚያ ማለትም ህዳር 1 ቀን 2014 ዓ/ም መክፈል ሲገባቸው እስከ አሁን ድረስ ያልከፈሉ ሲሆን ፤ በአመልካች መከፈል ሲገባው በተጠሪ የተከፈለ በድምሩ ብር 114,622.24 ተርን ኦቨር ታክስ እንዲከፍሉ ከኪራይ ውሉ ውጪ ያለ ተጠሪ እውቅናና ፍቃድ ህገወጥ ግንባታ እንዲሁም ነባር የግንብ አጥር ማፍረሳቸውንና እነዚህ ደግሞ መሰረታዊ የውል ጥሰት በመሆናቸው በ13/06/10 ዓ/ም የተደረገ የቤት ኪራይ ውል እንዲፈርስና አመልካች የመኖሪያ ቤቱን አሟልተው እንዲያስረክቡ፤ ተከሳሽ ውዝፍ ኪራይ ብር 90,000 እና ቤቱን እስኪመልሱ ድረስ ያለውን የኪራይ ሂሳብ በወር ብር 45,000 ታስቦ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍሉኝ፤ ቤቱን እስከሚመልሱ ቀን ድረስ የሚኖረውን ታክስና የፍጆታ ሂሳብ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍሉኝ የፈጸሙት ህገወጥ ግንባታ የሚያስከትለውን ማናቸውንም ወጪ ወይም ኪሳራ እንዲሸፍኑ ከወጪ ኪሳራ ጋር ይወሰንልኝ የሚል ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች በሰጡት መልስ ተጠሪ አልተከፈለኝም በማለት የጠየቁት የህዳር እና የታህሳስ ወር 2014 ዓ/ም የ2 ወር የቤት ኪራይ ክፍያ ሲሆን ሳይከፈል የቆየው በእኔ ጥፋት ወይም ቸልተኝነት ሳይሆን በተጠሪ በመንግስት ዘንድ የጸጥታና የኢኮኖሚ አሻጥር መፍጠር ምክንያት የንግድ ቤቱ በመታሸጉ ስራ መስራትና ኪራይ የህዳር እና የታህሳስ መክፈል ባለመቻሉ እንደሆነ በውላችንና በፌደራል ገቢዎች አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 16 መሰረት ቤቱን አድሼና አስፋፍቼ ለንግድ አከራይቼ በውሌ መሰረት በወቅቱ የቤት ኪራይ ለ4 አመት ስከፍል ቆይቻለው፡፡ ከግንቦት 1 ቀን 2013 ዓ/ም እስከ ጥቅምት 30 ቀን 2014 ዓ/ም ድረስ የከፈልኩትን የ6 ወር

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ኪራይ ብር 270,000 አከራይ ሲጠቀሙበት ቤቱ በመታሸጉ ምክንያት ቀድሞ የከፈሉኝ ተከራዮች የከፈሉትን ገንዘብ አስመልሰው ቤቱን ለቀው ሄደዋል፡፡ በመሆኑም ከሐምሌ 26 ቀን 2013 ዓ/ም እስከ ጥር 2 ቀን 2014 ዓ/ም ድረስ 5 ወር ከ5 ቀን ቤቱ በተጠሪ ስም በመታሸጉ ከ5 ተከራዮች አገኝ የነበረውን ገቢ ብር 369,200 አጥቻለው፡፡ ስለዚህ ከዚህ ገንዘብ ውስጥ ኪራይ ያልተከፈለበት የ62 ቀናት ተቀንሶ የ3 ወር ከ4 ቀን ብር 141,000 ያለአግባብ የከፈልኩት ሊመለስልኝ ወይም ሊቻቻልልኝ ይገባል፡፡ በተጠሪ በራሳቸው ችግር በስማቸው ቤቱ በታሸገበት ሁኔታ ላልሰራሁበት ቤት ወደፊት ከሚገኝ የኪራይ ገቢ ከነወለዱ ይክፈሉኝ ውሉ ተሰርዞም ቤቱን ያስረክቡኝ መባሉ ተገቢነት የለውም፡፡ ውል ስንፈጽምም ተርን ኦቨር ታክስን ጨምሮ ኪራዩን ከፍ በማድረግ ጥቅል ውል በተዋዋልንበት በድጋሚ የተርን ኦቨር  ታክስ ይከፈለኝ በሚል የተጠየቀው ዳኝነት ተከሳሽን አይመለከትም፡፡ የቤቱ ግንባታ የተሰራው ግን በተጠሪ ፍቃድ በውል በተደረገ ስምምነት እንዳዲስ ተስማምተን የተደረገ ነው ፤በመሆኑም ለ5 ወር ከ6 ቀን ቤቱ ታሽጎ የቆየ በመሆኑ ይኸው ጊዜ ከሚያዝያ 30 ቀን 2015 ዓ/ም በኋላ ባለው ጊዜ የማቻቻያና የችሮታ ጊዜ ሊሰጠው ይገባል ተብሎ እንዲወሰን በማለት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች ባቀረቡት የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ከግንቦት 1 ቀን 2013 ዓ/ም እስክ ጥቅምት 30 ቀን 2014 ዓ/ም ድረስ የ6 ወር የኪራይ ገንዘብ ብር 270,000 ለተጠሪ ለ6 ወር በከፈልኩት የቤት ኪራይ 2 ወር ከ26 ቀን እንደሰራሁ በተፈጠረው የጸጥታ ችግር ተጠሪ የጸጥታና የኢኮኖሚ አሻጥር በመፍጠር ተጠርጥረው ከሐምሌ 26 ቀን 2013 ዓ/ም እስከ ጥቅምት 30 ቀን 2014 ዓ/ም ለ5 ወር ከ6 ቀን የንግድ ቤቱ ታሽጓል፡፡ ቀሪው 3 ወር ከ4 ቀን ኪራይ የተከፈለበትን ጊዜ አልተጠቀምኩበትም፡፡ በተጠሪ ምክንያት ቤቱ በመታሸጉ ያከራየኋቸው ሰዎች የከፈሉትን ገንዘብ አስመልሰውኝ በመውጣታቸው ቤቱ በታሸገበት በ5 ወር ከ6 ቀን ጊዜ ውስጥ አገኝ የነበረውን ብር 369,200 አጥቻለው፡፡ በመሆኑም የከሳሽ ተከሳሽ ከከፈልኩት የ6 ወር ኪራይ ገንዘብ ብር 270,000 ላይ ያልሰራሁበትን የ3 ወር ከ4 ቀን ኪራይ ገንዘብ ብር 141,000 እንዲሁም በቤቱ መታሸግ ምክንያት ተከራዮች በመውጣታቸውና የተከፈለውንም የኪራይ ገቢ መልሰው በመውሰዳቸው ያጣሁትን ገንዘብ ብር 369,200 እንዲከፍሉኝ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ በአመልካች የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ላይ በሰጡት መልሳቸው ቤቱ ከመዘጋቱ በፊትም ሆነ በተዘጋ ጊዜ ዛሬ ድረስ በማናቸውም ወንጀል ተጠርጥሬ ታስሬ ወይም በፖሊስ ተጠይቄ አላውቅም ቤቱ የተዘጋውም የራሳቸው የተከሳሽ ከሳሽ ተከራይ የሆኑት አቶ አብርሀም ለገሰ የተባሉት ግለሰብ ለሌሎች አካላት ገንዘብ ያሰባስባሉ ተጠሪም እጃቸው አለበት የሚል የሀሰት ጥቆማ ለጸጥታ አካላት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በመስጠታቸው ነው፡፡ በመሆኑም ቤቱ ተዘግቶ እንዲከርም ያደረጉት ራሳቸው አመልካች በመሆናቸው የተዘጋውም በእኔ ምክንያት ወይም ጥፋት ስላልሆነ የኪራይ ገንዘቡን ለመመለስ አልገደድም ፤ የታጣ ገቢ ወይም የጉዳት ካሳ የምከፍልበት የህግም ሆነ የፍሬ ነገር ምክንያት የለም፡፡ በማለት መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡

በዚህ መልኩ ጉዳዩ የቀረበለት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ በሰጠው ውሳኔ አመልካች ለተከራዩት ቤት ኪራይ የመክፈል ግዴታ ብቻ ሳይሆን የ6 ወር በቅድሚያ የመክፈል ግዴታ እንዳለባቸው ፤በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1791 (2) በተመለከተው መልኩ ግዴታውን ያልፈጸሙት በቂ የሆነ ምክንያት መኖሩን ማስረዳት ብቻ ሳይሆን ኪራይ የመክፈል ግዴታቸውን ያልተወጡት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑን ገልጸው ያቀረቡት ክርክር እና ማስረጃ ባለመኖሩ  በተቃራኒው ቤቱ ሊታሸግ የቻለው በአመልካች ጥቆማ ምክንያት ስለመሆኑ ተጠሪ በምስክሮች በማስረዳታቸው ኪራይ እንዲከፍሉ ፤ከተጠሪ ጋር ባደረጉት የኪራይ ውል የየስድስት ወሩን የኪራይ ገንዘብ ክፍያ መክፈል እንዳለባቸው በግልጽ የተመለከተ በመሆኑና በውሉ ላይ የተቀመጠው የመክፈያ ጊዜ ወይም የግዴታ መፈጸሚያ ጊዜ ያለፈ በመሆኑ ተጠሪ ማስጠንቀቂያ መስጠት ሳያስፈልጋቸው ክስ አቅርበው ውሉ እንዲቋረጥላቸው ለማመልከት የሚችሉ በመሆኑ ግራ ቀኙ መካከል በቀን 13/06/2010 ዓ/ም የተደረገው የቤት ኪራይ ውል ስምምነት ሊፈርስ እንደሚገባው ፣ በውል በገቡት ግዴታ መሰረት የሰሯቸውን ክፍሎች ያለምንም ክፍያ ለተጠሪ እንዲያስረክቡና የተከራዩትንም ቤት ለቀው እንዲያስረክቡ ፤ አመልካች እንዲመለስላቸው የጠየቁትን የኪራይ ገንዘብ በተመለከተ በተጠሪ ጥፋት ወይም ወንጀል ምክንያት የታሸገ ስለመሆኑ በማስረጃ ያላረጋገጡ በመሆኑ ተጠሪ የኪራይ ገንዘቡን ለመመለስ የሚገደዱበት የህግ ምክንያት ባለመኖሩና በተጠሪ ምክንያት ያጡት ገቢ የደረሰባቸው ጉዳት ስለመኖሩ ያላረጋገጡ በመሆኑ ያጣሁት ገቢ ብር 369,200 ይከፈለኝ በማለት ያቀረቡት ዳኝነት ጥያቄ የህግም ሆነ የማስረጃ ድጋፍ የለውም በማለት ውድቅ በማድረግ  ውዝፍ ኪራይ አመልካች የሁለት ወራት ብር 90,000 ፣ቤቱን እስከሚያስረክቡ ድረስ በየወሩ ብር 45,000 ለተጠሪ እንዲከፈሉ፣ የተርንኦቨር ታክስ ክፍያ አመልካች እንዲከፍሉ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ዉሳኔ ያልተስማሙት የአሁን አመልካችም የይግባኝ ቅሬታ ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ በዝርዝር የቀረበለትን የይግባኝ ቅሬታ መርምሮ የተርንኦቨር ታክስ ክፍያን በሚመለከት ብቻ ያስቀርባል በማለት የቀሩትን  የይግባኝ ቅሬታ ነጥቦችን ሳይቀበላቸው ቀርቷል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የሰበር ማመልከቻውም የቀረበው በዚህ ላይ ሲሆን የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘት በአጭሩ፡- የስር ፍ/ቤት የሁለት ወር ውዝፍ ኪራይ ብር 90,000 /ዘጠና ሽህ በር /እና ቤቱን እስከማስረክብ ድረስ በየወሩ ብር 45,000 ሂሳብ እየታሰበ መክፈል አለብህ ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ ፣ የስር ፍ/ቤት የተከራየሁትን የንግድ ቤት ቀጥር 422 የሆነውን ቤት እና በስምምነት ከሰራኋቸው ቤቶች ጋር የውሉ ዘመን ሳያልቅ ይፍረስ ተብሎ ክስ ባልቀረበበት ሁኔታ እንዳስረክብ መወሰኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1731(1) መሠረት ውል በተዋዋይ ወገኖች መካከል ህግ ነው የሚለውን ደንጋጌን የጣሰና በተከራካሪ ወገኖች ያልተነሣን እና ለክርክር መሰረት የሆኑትን የህግ ድንጋጌዎች በሚቃረን ሁኔታ የሰጠው ውሳኔ እንዲሻርልኝ፣ አመልካች ለስር ፍ/ቤት ከተጠሪዋ ላይ ከተከራየሁት የንግድ ቤት ኪራይ የ6 ወራት በብር 45,000 ሂሳብ ብር 270,000(ሁለት መቶ ሰባ ሺህ) ከግንቦት 1 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ጥቅምት 30 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ የከፈልኩና 2 ወራት ከ26 ቀናት ብቻ እንደሰራሁበት በተጠሪዋ ችግር የንግድ ቤቱ በፀጥታ ሀይሎች ከሐምሌ 26 ቀን 2013 ዓ.ም እስከ ጥር 02 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ ለ5 ወራት ከ6 ቀናት የታሸገ መሆኑን በመግለፅና ቀሪውን የ3 ወራት ከ4 ቀናት ያለውን የውል ጊዜ ብር 141,000 ሳልጠቀምበት የታሸገ መሆኑንና ከእኔ የተከራዩት የተከራይ ተከራዮችም የከፈሉኝን ብር 369,200 ብር በመመለሴ ምክንያት ያጣሁትን የወር ኪራይ ገቢ በተጠሪ ላይ እንዲታሰብ ወይም እንዲቻቻል ያቀረብኩትን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አላግባብ ከህግ ውጭ ውድቅ መደረጉ ተገቢ ባለመሆኑ በጠየቅሁት ዳኝነት መሠረት ሊወሰንልኝ ይገባል የሚል ነዉ፡፡

የሰበር ሰሚ ችሎቱም አመልካች በኪራይ ዉል የያዙትን የንግድ ቤት በተመለከተ መንግስት በወቅቱ በነበረዉ ሁኔታ የጸጥታና ኢኮኖሚ አሻጥር ተፈጽሟል በሚል ምክንያት መዘጋቱ ተነግሮ እያለ አመልካች የንግድ ቤቱ ታሽጎ ለቆየበት ጊዜ ዉዝፍ ኪራይ ገንዘብ እንዲከፍሉ የተወሰነበትን አግባብነት ለማጣራት ያስቀርባል ተብሎ ግራ ቀኑ ክርክር አድርገዉበታል፡፡

ተጠሪ ቀርበው በሰጡት መልስ አመልካች ክርክራቸውን ማለትም ቤቱ የታሸገው ተጠሪ በአሻጥር በመጠርጠሬ ምክንያት መሆኑን የማስረዳት ሸክም አለባቸው፡፡ የስር ፍ/ቤት በዚህ ነጥብ ላይ የግራ ቀኙን ምስክሮች ከመስማት በተጨማሪ የሚመለከተውን የመንግስት አካል ቤቱ ስለታሸገበት ምክንያት ጠይቆ በቀረበው ምላሽ ላይ ቤቱ ከፀጥታ ችግር ጋር በተያያዘ ታሽጎ መቆየቱ ከመገለፁ በስተቀር የታሸገው በተጠሪ ምክንያት ነው አልተባለም፡፡ አመልካች ኪራዩን አልከፈፍልም የሚሉት ቤቱ የታሸገው በተጠሪ ምክንያት ነው በማለት ስለሆነ እርሳቸው ቤቱ የታሸገው በተጠሪ ምክንያት መሆኑን ካላስረዱ ኪራዩን የማይከፍሉበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች ይህንን ፍሬ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ነገር የማስረዳት ሸክማቸውን ሳይወጡ በመቅረታቸው ኪራዩን እንዲከፍሉ መወሰኑ ተገቢና ህጋዊ ነው፡፡ ቤቱ የታሸገው በተጠሪ ምክንያት ስላልሆነ የታሸገበት ጊዜ ኪራይ የሚወራረድበት ምክንያት የለም፡፡ አመልካቹ ቤቱን አዘግተው ተከራያቸውን አቶ አብርሃምን ለመጉዳትና ለማጉላላት አስበው በክፉ ልቦና ተነሳስተው ራሳቸው በሰጡት ጥቆማ ምክንያት አዘግተው ማቆየታቸውን ተጠሪ በስር ፍ/ቤት አስረድቻለሁ፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቱ በዚህ ረገድ የያዘው ጭብጥም ሆነ የሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ባለመሆኑ የሚነቀፍበት አንዳችም ምክንያት የለም ፡፡ ኪራዩ አለመከፈሉ የውል ጥሰት በመሆኑም ውሉ ይሰረዝልኝ ስል የጠየቅኩት ህጋዊ ዳኝነት ሲሆን ፍ/ቤቱም አመልካች ኪራዩን ከፍያለሁ የሚል ክርክርም ሆነ ማስረጃ እስካላቀረቡ ድረስ ኪራዩ አለመከፈሉን አረጋግጦ ውሉ እንዲሰረዝና ቤቱን አመልካች ለተጠሪ እንዲያስረክቡ መወሰኑ በተጠየቀው ዳኝነት መሠረት የተሰጠ ፍርድ ስለሆነ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ አመልካች ቤቱ ለተዘጋበት ጊዜ የከፈልኩት ኪራይ ወቅቱን ጠብቄ መክፈል ሲገባኝ ሳልከፍል የቀረሁበት ጊዜ ኪራይ ሆኖ ይታሰብልኝ የሚል ክርክር በበታች ፍ/ቤትም ሆነ በይግባኝ አላቀረቡም፡፡ አመልካች በስር ያላቀረቡትን ይህንን ክርክር በሰበር ደረጃ ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲያቀርቡ የሚፈቅድላቸው የሥነ ሥርዓት ህግ ድንጋጌም ሆነ የሰበር ችሎት የህግ ትርጉም ስለሌለ ፍ/ቤቱ የሰጠው ያልተጠየቀውን ዳኝነት ነው ሲሉ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡አመልካች በስር ፍ/ቤት በቤቱ መታሸግ ምክንያት ለተከራዮች የመለሱት ገንዘብ መኖሩን በማስረጃ ማረጋገጥ አልቻሉም፡፡ ስለሆነም የስር ፍ/ቤት በውሳኔው የፈፀመው መሠረታዊ የህግ ስህተት አለመኖሩን እና አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ በሐሰት የቀረበ መሆኑን ከግምት በማስገባት አመልካች ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ እንዲያፀናልኝ  በማለት ተከራክረዋል፡፡

የሰበር አመልካችም የሰበር ክርክራቸውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርበው ክርክሩ በዚሁ ተጠቃሏል፡፡

እኛም ቅሬታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ በስር ፍርድ ቤት ከተደረገዉ ክርክር የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እንዲሁም አግባብነት ካለዉ ህግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል ፡፡ እንደመረመርነዉም ቅሬታዉ ያስቀርባል ሲባል የተያዘዉ ጭብጥ አመልካች በኪራይ ዉል የያዙትን የንግድ ቤት በተመለከተ መንግስት በወቅቱ በነበረዉ ሁኔታ የጸጥታና ኢኮኖሚ አሻጥር ተፈጽሟል በሚል ምክንያት መዘጋቱ ተነግሮ እያለ አመልካች የንግድ ቤቱ ታሽጎ ለቆየበት ጊዜ ዉዝፍ ኪራይ ገንዘብ እንዲከፍሉ የተወሰነበትን አግባብነት ለመመርመር በመሆኑ ከዚሁ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምረናል እንደመረመርነዉም የሰበር አመልካች ከግንቦት 1 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ እስከ

ጥቅምት 30 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ ኪራይ የከፈልኩና 2 ወራት ከ26 ቀናት ብቻ እንደሰራሁበት በተጠሪዋ ችግር ምክንያት የንግድ ቤቱ በፀጥታ ሀይሎች ከሐምሌ 26 ቀን 2013 ዓ.ም እስከ ጥቅምት 30 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ ለ5 ወራት ከ6 ቀናት የታሸገ መሆኑን በመግለፅና ቤቱ ለታሸገበት ኪራይ ልከፍል አይገባም በማለት የሚከራከሩት ቤቱ የታሸገዉ በተጠሪ ምክንያት በመንግስት ትዕዛዝ ነዉ በማለት ሲሁን የሰበር ተጠሪ በበኩላቸዉ ደግሞ ቤቱ የታሸገዉ በእኔ ምክንያት ሳይሆን በራሳቸዉ በሰበር አመልካች አሻጥር ስለሆነ ለታሸገበት ግዜ ጭምር ኪራይ ሊከፍሉ ይገባል ተብሎ መወሰኑ ስህተት አይደለም በማለት የሚከራከሩ ናቸዉ ፡፡ ችሎቱ በበኩሉ እንደተመለከተዉ አከራካሪዉ ቤት ለ5ወራት ከ6ቀን በመንግስት መታሸጉ ግራቀኙን ያከራከረ ጉዳይ አይደለም የሚያከራክረዉ ጭብጥ በማን ምክንያት ታሸገ የሚለዉ ሲሆን ፡፡ ተጠሪ ቤቱ የታሸገዉ በአመልካችም ጥቆማ መሆኑን ያረጋገጥሁ ስለሆነ ጥፋቱ የእሳቸዉ እንጅ የእኔ አይደለም በማለት የሚከራከሩ ሲሆን የስር ፍርድ ቤቶችም ይህንኑ መቀበላቸዉን ተረድተናል ፡፡ ይሁን እና ለዚህ ጉዳይ መታየት የሚገባዉ የጠቋሚዉ ማንነት ሳይሆን ቤቱን የመንግስት አካል እንዲታሸግ ያደረገበት አብይ ምክንያት ሲሆን ምክንያት ተደርጎ የተቀመጠዉም ተጠሪ በመንግስት ዘንድ የጸጥታ እና የኢኮኖሚ አሻጥር ፈጥረዋል በሚል ተጠርጥረዉ መሆኑ ነዉ ፡፡ ይህ ሁኔታ የሰበር አመልካች ሊመልሱት የማይችሉት ከአቅማቸዉ በላይ የሆነ የመንግስት አካል የፈጸመዉ ተግባር በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1791(2) እና 1793(ለ) ድንጋጌ ኃላፊነት የሚያስከትልባቸዉ አይደለም ፡፡ በሌላ በኩል አመልካች ቤቱን የተከራዩት ለንግድ አገልግሎት ሲሆን ቤቱ በታሸገበት ወቅት ይህንን ንግድ አገልግሎት መስጠት የሚችሉበት ምንም ዓይነት ሁኔታ ሊኖር እንደማይችል ግልጽ ነዉ ፡፡በአከራካሪዉ የንግድ ቤት ምንም አይነት ስራ ሳይሰሩ ኪራይ ሊከፍሉ ይገባል ሊባሉ የሚችሉበት የአመክንዮም ሆነ የህግ ምክንያት የለም ፡፡ ተጠሪ ከሰበር አመልካች ይልቅ እሳቸዉ የቤቱ ባለቤት እንደመሆናቸዉ መጠን በወቅቱ ቤቱ በማንም ጥቆማ ቢሆን መታሸግ የለበትም ብለዉ የአሸገዉን የመንግስት አካል ሳይጠይቁ ቆይተዉ አሁን በታሸገበት ግዜም ቢሆን ኪራይ ሊቋረጥብኝ አይገባም እንዲሁም በእኔ ምክንያት አልታሸገም የሚለዉ ክርክራቸዉ የህግም ሆነ የማስረጃ መሰረት ያለዉ አይደለም ፡፡

ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች የሰበር አመልካች አከራካሪዉ ቤት ታሽጎ ለቆየበት ግዜ ኪራይ ሊከፈል ይገባል በማለት የስር ፍርድ ቤቶች የደረሱበት ድምዳሜ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በማለት ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

ዉሳኔ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በስር ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 102513 ነሐሴ 27 ቀን 2014 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 297177 የካትት 21 ቀን 2015 ዓ/ም በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 337 መሰረት በትዕዛዝ የጸናዉ ፍርድ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህቁ 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡

የሰበር አመልካች አከራካሪዉ ቤት በመንግስት አካል ታሽጎ ለቆየበት 5ወር ከ6ቀን ጊዜ ኪራይ ሊከፍል አይገባም ተብሎ ተወስኗል፡፡

ቀሪዉ የስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ አልተነካም፡፡

በመዝገቡ ላይ ተሰጥቶ የነበረዉ የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል ፡፡ ለሚመለከተዉ ክፍል ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ.245126

ጥቅምት 07 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች፡-ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

ሠናይት አድነው

ሀፊዝ አባጀማል

አመልካች ፡- አቶ ተስፋዬ አሰፋ ጠበቃ ሹምአለም ጌታቸው ቀረቡ

ተጠሪ ፡- አቶ መርሻ ኃይሉ ጠበቃ ተስፋዬ ታደሰ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍርድ</u>

ጉዳዩ የዕቃ ሽያጭ ውልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲጀመር የአሁን አመልካች ከሳሽ፣ የአሁን ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

አመልካች በፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ በአጭር ሥነ ሥርዓት እንዲታይ ባቀረቡት ክስ ከተጠሪ ጋር ባለን የንግድ ግንኙነት በዱቤ ለገዙት ለውሃ ማሸጊያ ፕላስቲክ የሚሆን ባለ 27 ግራም ፕሪፎርም ምርት የቅድሚያ ክፍያ ከከፈሉ በኂላ ለቀሪው ብር 2,218,000.00 ክፍያነት

<u>ማስታወሻ</u>፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ቁጥራቸው 25544469 እና 25544471 የሆነ 2 ቼኮችን የሰጡኝ ሲሆን የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሚያዚያ 26 ቀን 2012 ዓ.ም እና መስከረም 04 ቀን 2013 ዓ.ም ለክፍያ የሚሆን በቂ ስንቅ እንደሌለ ከገለፀልኝ በኂላ ተጠሪ ከዕዳው ተቀናሽ የሚደረግ ብር 759,000.00 የሚያወጣ ውሃ አስረክበውኝ ቀሪ ዕዳውን ብር 1,459,000.00 ለመክፈል ፍቃደኛ ባለመሆናቸው ጉዳዩ በአጭር ስነ ስረአት ታይቶ እዳው መከፈል ከነበረበት ከሚያዚያ 2012 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ፣ የጠበቃ አበል እና ሌሎች ወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፍሉኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ በበኩላቸው መከላከያ ለማቅረብ ፍ/ቤቱን ፍቃድ ጠይቀው መከላከያውን እንዲያቀርቡ ጉዳዩም በመደበኛው የሙግት አመራር እንዲመራ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡ በዚህ መሰረት ተጠሪ ባቀረቡት መልስ ቼኮቹ የተሰጡት በድርጅት ስም በመሆኑ አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ ለማቅረብ መብትና ጥቅም የላቸውም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበው፣ ክስ ከቀረበ በኂላ ብር 359,000.00 ክፍያ ስለተፈፀመ ክስ ከቀረበበት ገንዘብ ላይ ተቀናሽ ሊደረግ ይገባል፣ በቼኩ ላይ የተገለፀው ክፍያ ከመከፈሉ በፊት አመልካች ምርቱን በቼኩ ላይ ከተገለፀው ገንዘብ ጋር በሚጣጣም መልኩ ማቅረብ ያለባቸው ቢሆንም አመልካች 2,745,600 ፕሪፎርም ማቅረብ ሲገባቸው 2,687,300 ፕሪፎርም ብቻ በማቅረብ ብር 362,670.00 ዋጋ ያለው ብዛቱ 172,700 ምርት (ፕሪፎርም) ያላቀረቡ ስለሆነ ባላቀረቡት ምርት ላይ ክፍያ ሊጠይቁ ስለማይገባ ከተጠየቀው ክፍያ ተቀናሽ ሊደረግ ይገባል በማለት አማራጭ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ተጠሪ ያቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በብይን ውድቅ በማድረግ፣ ክስ ከቀረበ በኂላ ተጠሪ ብር 359,000.00 መክፈላቸው እና ከብር 362,670.00 ውጪ ያለው ዕዳም ስለታመነ ተጠሪ ብር 737,330.00 ለአመልካች እንዲከፍሉ ከፊል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ግራ ቀኙ በተካካዱበት ብር 362,670.00 ላይ ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙ ያቀረቡትን የምስክሮች ቃል እና የሰነድ ማስረጃ በመመርመር ቼኮቹ ክፍያ የሚጠየቁበት ሳይሆን በመያዣ ተይዘው በቀረበው የምርት አቅርቦት ልክ ክፍያ ሲፈፀም የነበረ መሆኑን እና ክርክር የተነሳበትን ምርት አመልካች አስረክቤያለሁ በማለት የሚከራከሩት እና በበለጠ የተረጋገጠውም ርክክብ እንዲያደርግ በተጠሪ ለተወከለው ሰው ሳይሆን ተጠሪ ላልወከሉት ሌላ ሰው መሆኑን ተጠሪ በበለጠ በማስረዳት አመልካች ብር 362,670.00 የሚያወጣ ምርት ለተጠሪ ማስረከባቸው አልተረጋገጠም በማለት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ደምድሞ ተጠሪ ክፍያውን ለአመልካች ሊከፍሉ አይገደዱም በማለት እና የወጪ እና ኪሳራንም ክርክር ውድቅ በማድረግ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካችም በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካችም በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ መጋቢት 27 ቀን 2015 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ የሰበር አቤቱታቸውም ተጠሪ ቼኩን ለዕዳ መክፍያነት የሰጡ መሆኑን፤ ተጠሪ የተረከቡት ጥሬ ምርት ጉድለት የለበትም እንጂ ቢኖርበትም በቀላሉ የሚለይ ሆኖ ሳለ በራሳቸው ቸልተኝነት ጉድለት መኖሩን በማረጋገጥ ማሳወቅ ያለባቸውና በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ክስ ማቅረብ ሲገባቸው ይህን ሳያደርጉ ጉድለት አለ ብለው መከራከር እንደማይችሉ መቃወሚያ ብናቀርብም በዝምታ ታልፏል፡፡ ርክክቡ ተጠሪ ርክክብ እንዲያደርጉ በወከሏቸው ግለሰብና በሹፌሮቻቸው በኩል መፈፀሙን በግራ ቀኙ የሰውና የሰነድ ማስረጃ ተረጋግጦ ባለበት ሁኔታና ተጠሪም ይህን በማስተባበል ሳይከራከሩ የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የማስረጃ ምዘና መርህን ያልተከተለ ነው፡፡ ወለድ ሊከፈለን ይገባል በማለት ዳኝነት ጠይቀን በዝምታ መታለፉ እንዲሁም  በሕግ አግባብ ወጪና ኪሳራ ሊከፈለን ሲገባ አላግባብ ተቻቻሉ መባሉ አግባብነት የሌለው ስለሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ እንዲሻር፤ቀሪ ክፍያው ብር 362,670.00 ከነወለዱ እንዲከፍል እንዲሁም ባጠቃላይ ክስ የቀረበበትን የገንዘብ መጠን መከፈል ከነበረበት 20/01/12 ዓ.ም ጀምሮ የሚታሰብ ወለድ እንዲከፍል በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ሰበር ሰሚ ችሎቱም ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ብር 360,670.00 ተጠሪ ለአመልካች ሊከፍሉ አይገባም በማለት ሲወሰን የተሰጠው ምክንያት በተጠሪ ለአመልካች መሰጠታቸው ያልተካደው ሁለቱ ቼኮች በማስረጃ ረገድ ሊኖራቸው የሚገባውን ዋጋ (probative value) ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለመሆኑ እንዲሁም ለአመልካች የሚታሰብ ወለድ መኖር አለመኖሩንና ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ መባሉ በአግባብ ነው ወይስ አይደለም የሚሉ ነጥቦችን አጣርቶ ለመወሰን ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በበኩላቸው በሰጡት መልስ አመልካች ለወሰዱት ቼክ ምክንያት የሆነውን ግዴታቸውን አለመወጣታቸውን፣ ጉድለት መኖሩን ተጠሪ በወቅቱ ለአመልካች ማሳወቃችንን፣ ጉድለትን

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በተመለከተ የተነሳ የሕግ ክርክር አለመቅረቡንና ከፍርድ ቤት ውጪ ክፍያም የተፈፀመ መሆኑን በማረጋገጥ ስለሆነ ወለድ ከ20/01/2012 ዓ.ም ጀምሮ የሚከፈልበት አግባብ ካለመኖሩም በላይ ቼክ በማስረጃነት ረገድ ሊኖረው የሚገባውን ዋጋ ከግምት በማስገባት የተሰጠ ውሳኔ ነው። የሥር ፍ/ቤት መጋቢት 30 ቀን 2014 ዓ.ም በከፊል በሰጠው ውሳኔ ወለድን ጭምር በማሰብ ውሳኔ ሰጥቶ በዚሁ አግባብ ተፈፅሟል። የስር ፍ/ቤቶች የቀረበውን ክርክር የአመልካችን ግዴታ አለመወጣት እንዲሁም ከቀረበው ክርክር አንፃር ተጠሪ ለአመልካች ሊከፍሉ የሚገባ እዳ ያለመኖሩን የተሰጠውን ውሳኔ ከግምት በማስገባት ወጪና ኪሳራ ሊከፈል አይገባም በማለት ውሳኔ መሰጠቱ ላይ በሥር ፍርድ ቤት የተፈፀመ ስህተት ባለመኖሩ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል።

አመልካችም አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል። የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል እኛም ከግራ ቀኙ አቤቱታና መልስ እንዲሁም ለጉዳዩ ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች አንፃር መርምረነዋል። እንደመረመርነውም በግራ ቀኙ መካከል የንግድ ግንኙነት የነበረ መሆኑ እና በዚህም መነሻነት ተጠሪ በዱቤ የገዙት የውሃ ማሸጊያ ፕላስቲክ ስለመኖሩ እና ከዚህም ውስጥ አሁን ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት መከራከሪያ የሆነው ገንዘብ ብር 362,670.00 ተጠሪ ያልከፈሉ መሆናቸው አከራካሪ አይደለም ግራ ቀኙን ያከራከረው ጉዳይ አመልካች በውሉ መሰረት ለተጠሪ የተባለውን ምርት ያስረከብን ስለሆነ እና ተጠሪም ለክፍያ የሚሆን ቼክ ቢሰጡም ቼኩ ለክፍያ ባንክ ሲቀርብ ስንቅ የሌለው በመሆኑ ተጠሪ ያልከፈሉትን ቀሪውን ገንዘብ ሊከፍሉን ይገባል የሚል ነው።

የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ሰምቶ የበለጠ የተረጋገጠው ተጠሪ የሰጡት ቼክ ለዋስትና እንጂ ለክፍያ ያለመሆኑ፣ ለዚህም በቼኩ ከተገለጸው ገንዘብ ውስጥ አልተከፈለም ተብሎ ዳኝነት የተጠየቀው አልተከፈለም በተባለው ቀሪ ገንዘብ ላይ ብቻ መሆኑ፣ በተጨማሪ አመልካች አሁን ለሰበር መከራከሪያ የሆነውን ገንዘብ ግምት የሚሆን ምርት ለተጠሪ ያለማስረከባቸው በበለጠ ተረጋግጧል በማለት ደምድሞ ተጠሪ ለዚህ ሰበር ችሎት መከራከሪያ የሆነውን ገንዘብ ብር 362,670.00 ሊከፍሉ አይገባም በማለት በሰጠው ውሳኔ የአሁን አመልካች ቅር ተሰኝተው ለፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታቸውን ቢያቀርቡም ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ አመልካች ያቀረቡትን የይግባኝ ቅሬታ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 337ን በመጥቀስ ውድቅ በማድረግ ትእዛዝ መስጠቱን ከስር ፍርድ ቤቶች የውሳኔ ግልባጮች መረዳት ችለናል።

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በመሆኑም አመልካች በውሉ መሰረት የተባለውን ምርት በሙሉ ለተጠሪ በማስረከብ ግዴታችንን ተወጥተን እያለ ተጠሪ ያልከፈሉትን ቀሪ ክፍያ ሊከፍሉ አይገባም ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም ሊሻር ይገባል በማለት ያቀረቡትን ቅሬታ ከሰበር ሰሚው ችሎት ስልጣን አንጻር ስንመረምረው በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ ላይ እንደተደነገገው የሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን የመጨረሻ ዉሳኔ በተሰጠባቸዉ ጉዳዮች ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞ ሲገኝ ይህንኑ በማረም ላይ የተገደበ ከመሆኑም በተጨማሪ በሰበር ሊታረም የሚገባ መሰረታዊ የህግ ስህተት የሚያሰኙት ምክንያቶች በፌደራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2/4/ እና 10 ተዘርዝረው የሚገኙት ናቸው የእነዚህ የህግ ድንጋጌዎች ይዘት ሰበር ሰሚ ችሎት የተቋቋመበትን ዓላማ ማለትም ወጥ የህግ አተረጓጎም እንዲኖር እና የዉሳኔዎችን ተገማችነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በመስጠት እንዲሰራ ከተዘረጋው ከሰበር ስርዓት መሰረታዊ ዓላማም የምንገነዘበዉ ጉዳይ ነዉ፡፡

በተጨማሪም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅጽ 9 በመዝገብ ቁጥር 41526 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ከዚህ ሁሉ አንጻር ስናየው ሰበር ሰሚ ችሎቱ የፍሬ ነገር ክርክር የማጣራት፣ ማስረጃ የመመርመር እና የመመዘን ስልጣን በህግ ያልተሰጠው መሆኑን ነዉ፡፡ ስለሆነም አመልካቾች በዚህ ረገድ ያቀረቡት ቅሬታ የፍሬ ነገር እና የማስረጃ ምዘና ላይ ያተኮረ በመሆኑ በዚህ ችሎት ሊመረመር እና ሊታይ የሚገባው ሆኖ አላገኘነውም፡ በመሆኑም ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ዉሳኔ**

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 236488 መጋቢት 13 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠዉን ውሳኔ በማጽናት የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡

2.በዚህ ፍርድ ቤት ለተደረገዉ ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡
3.የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፍ/ደ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ፡245259

6/2/2017

ዳኞች ሺመክት አሰፋ

ገበየሁ ፈለቀ

አለማየሁ ሹናራ

ተናኜ ጥላሁን

ዘውዲቱ ታደሰ

አመልካች፦ተመስገን ድንጋጎ እና ቤተሰቡ ሃ/የተ/የግ/ማህበር ጠበቃ አቶ ክፍሌ ታደሰ ቀረቡ

ተጠሪ፦ሰናይት እሸቱ የአቶ እሸቱ ሰለሞን ወልደየስ ባለቤት እና የህጻን ናኦል ሰለሞን እና የማራናታ ሰለሞን አሳዳጊ ጠበቃ አቶ ፍቃዱ ይልማ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

**ፍርድ**

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በኦ/ጠ/ፍ/ቤት ምስራቅ ኦሮሚያ ቋሚ ችሎት ሆኖ አመልካች ተከሳሽ ሲሆን ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል።ተጠሪ በቀን 8/4/2010 ዓ ም አሻሽለው ያቀረቡት ክስ ባለቤቴ ሰለሞን ወልደየስ መኪና ሲያሽከረክር በቀን 29/3/2013 ዓም በአመልካች መኪና ተገጭቶ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በመሞቱ እድሜው 32 ዓመት የነበረ በመሆኑ የወር ደሞዙ 20,000 (ሃያ ሺ) ስለነበር  እስከ 60 ዓመት ስለሚኖር በህይወት ቢኖር ሊከፍለን ይችል የነበረው በዚሁ ተባዝቶ  ለተጠሪና እና ለልጆቻቸው በፍ/ህ/ቁ፣2095 መሰረት ካሳ፣ በተጨማሪም የቀብር ማስፈጸሚያና ለ40 ስነ ስርዓት ዝግጅት ወጪዎች እንዲሁም የጠበቃ አበል ጭምር ተደምሮ አመልካች እንዲከፍል ተብሎ እንዲወሰን የቀረበ ነው፡፡

አመልካች በሰጠው መልስ የተጠሪ ባል ደምወዙ 20000(ሀያ ሺ) ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ የለም፣ 60 አመት ሊኖር ይችል እንደነበረም ማረጋገጫ የለም፣ካሳ ክፍያው ሊጠየቅ የሚገባውም በቀለብ መልክ ነው፣ተጠሪ ሰርቶ መብላት የማይችሉበት ምክንያት ካለ ብቻ ነው ለራሳቸው ቀለብ መጠየቅ የሚችሉት፡፡እንዲሁም ተሽከርካሪው የኢንሹራንሽ ሽፍን ያለው በመሆኑ ሉሲ ኢንሹራንስ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ፣43(1) መሰረት ጣልቃ እንዲገባ ጠይቆ፣ በአጠቃላይ ተጠሪ ያቀረቧቸው ወጪዎች እና የዋጋ ግምቶች የተጋነኑ መሆኑን በመግለጽ ተከራከረ፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ የተጠሪ ባለቤት በአመልካች መኪና መገጨቱንና ጉዳት መድረሱን ተረጋግጦዋል በማለት ነገር ግን ተጠሪ ለራሳቸው የጠየቁትን ወጪ በተመለከተ ተጠሪ ሰርተው መብላት የማይችሉ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነገር የሌለ በመሆኑ ውድቅ እንዲሆን ወሰነ፡፡

ለህጻናቱ አባታቸው በሂወት ቢኖር ለእያንዳንዳቸው በወር ብር 2,500 (ሁለት ሺ አምስት መቶ) ያወጣ እንደነበር በመያዝ እድሜያቸው 18 ዓመት እስኪሞላቸው ድረስ የሚከፈላቸው ብር እና የቀብር ወጪ በርትእ 70,000 (ሰባ ሺ ብር) በመውሰድ በጠቅላላ በድምሩ ብር 852,000 (ስምንት መቶ አምሳ ሁለት ሺ ብር) የጠበቃ አበል 15% እና ወጪ ኪሳራ የዳኝነት ተጨምሮ እንዲከፍሉ ሲወስን፣ ከዚህ ውስጥ የስር ጣልቃ ገብ ሉሲ ኢንሹራንስ ብር 40,000 (አርባ ሺ ብር) እንዲከፍል በማለት ወሰነ፡፡አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት አቅርበው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ፣337 መሰረት አጸናው፡፡

የሰበር ችሎቱም በቀረበለት አቤቱታ ላይ ተመስርቶ ለሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነው የሟች አቶ ሰለሞን ወልደየስ የወር ደሞዝ ብር 2500 (ሁለት ሺ አምስት መቶ ብር) መሆኑን በመ ቁ፣32183 በቀን 14/4/2014 ዓም ውሳኔ ተሰጥቶ እያለ አሁን በተያዘው ጉዳይ ለሟች ሁለት ልጆች በየወሩ ለያንዳንዳቸው  ብር 2500 ( ሁለት ሺ አምስት መቶ) ይሰጥ ነበር ተብሎ  የቀለብ ካሳ የመወሰኑን አግባብነት እንደ ጭብጥ በመያዝ ያስቀርባል በማለት የግራ ቀኙን መልስ እና የመልስ መልስ በማስቀረብ አከራክሮዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክር ይዘት አጠር ባለ መልኩ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም የቀረበውን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ፣በዚህ መዝገብ ከተያዘው ጭብጥና እና ለጉዳዩ አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሯል፡፡አመልካች ያቀረበው የቅሬታ ነጥብ ከአንድ በላይ ቢሆንም፣ ውሳኔ የሰጠነው መዝገቡ ሲያስቀርብ በተያዘው ጭብጥ ላይ ብቻ ተመስርተን ነው፡፡

በአሰሪና ሰራተኛ ህግ ተጠሪ ከአሰሪ ለጠየቁት ካሳ አሰሪው የሟች ደሞዝ ብር 2500(ሁለት ሺ አምስት መቶ) ነበረ በማለት ባቀረበው ላይ በመመስረት በመ/ቁ32183 ተወስኖ ለተጠሪ ካሳ ብር 155000(አንድ መቶ አምሳአምስት ሺ) የተወሰነ ስለመሆኑ ከክርክሩ ተረድተናል፡፡ይህ እንዳለ ሆኖ ተጠሪ በዚህ ችሎት ባቀረቡት ክርክር የሀረርጌ ህዝብ ማመላለሻ አስጫኝ ማህበር ሟች ከጅጅጋ አዲስአበባ በወር ስምንት ግዜ እንደሚሄድና አንድ ግዜ ሲሄድ ብር 2500(ሁለት ሺ አምስት መቶ) እንደሚያገኝ፣ በወር ስምንት ግዜ ሲሄድም ብር 20000(ሀያ ሺ) ያገኝ እንደነበረ ማስረጃ ሰጥቶ ነው የተወሰነልኝ ብለው ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ደግሞ በመልስ መልሱ ይህ ማስረጃ አልቀረበም አላለም፡፡ ስለዚህ የሟች ደሞዝ 2500(ሁለት ሺ አምስት መቶ) የነበረ ቢሆንም መኪና በመያዝ ወደጅጅጋ በሄደ ቁጥር ያገኝ ነበር ተብሎ ከተረጋገጠው የሟች ገቢ አንጻር ለሁለት ልጆቹ በየወሩ ለቀለብ ለያንዳንዳቸው ብር 2500(ሁለት ሺ አምስት መቶ) መክፈል የማይችል ሰው ነበር ለማለት የሚቻል ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም ብለን ከዚህ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

- የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 370401 በታህሳስ 15/2015 የወሰነውና፣የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 240952 በመጋቢት 8/2015 ያጸናው ውሳኔ ተገቢ ሆኖ ስላገኘነው በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት አጽንተነዋል፡፡
- በዚህ መዝገብ በሀምሌ 19/2015 የተሰጠውን እግድ አንስተናል፡፡ እግድ ለተላለፈላቸው ክፍሎች እግዱ መነሳቱ ይጻፍ፡፡
- የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ ይቻቻሉ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፍ/ደ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ.መ.ቁ 245402

ጥቅምት 08 ቀን 2017 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** እትመት አሠፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

ሐብታሙ እርቅይሁን

አመልካች፡- የፋጡማ ሙህዬ ተተኪ ወራሽ መሀመድ እንድሪስ

ተጠሪ፡- አቶ አህመድ አብዱ

መዝገቡ ለፍርድ የተቀጠረ ነው፡፡ በዚሁ አግባብ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካች ጥቅምት 02 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 0329067 የካቲት 28 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ በሌለበት ታይቶ የተሰጠን ውሳኔ ለማስነሳት የቀረበን አቤቱታ የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች በቃሉ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 01-15021 የተሰጠውን ፍርድ እና ብይን በመቃወም በየደረጃው ላሉ ፍርድ ቤቶች ቅሬታ አቅርበዋል፡፡ በአመልካች በኩል በሰ.መ.ቁ 0329067 የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ያስቀርባል ካለ በኋላ ለተጠሪ መጥሪያ ልኮ ተጠሪ ስላልቀረበ ጉዳዩን

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በሌለበት አይቶ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን ውሳኔ ሽሮ ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ነው ሲል ወስኗል፡፡

ይህ ውሳኔ መሰጠቱን ተከትሎ ተጠሪ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መልስ የመስጠት መብቱ ታልፎ የተሰጠው ውሳኔ ቀሪ ሆኖ በጉዳዩ ላይ መልስ ሰጥቶ እንዲወሰን ሲል አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ሰበር ሰሚ ችሎቱም የተጠሪን አቤቱታ ከመረመረ በኋላ የተጠሪን መልስ የመስጠት መብት የነፈገው እና የመጨረሻ ውሳኔ የሰጠው ይህ ችሎት ቢሆንም ችሎቱ ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመርመር እና የመመዘን ስልጣን ስለሌለው ተጠሪ አለኝ የሚሉትን መልስ የመስጠት መብት ይከበርልኝ ጥያቄ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መደበኛው ችሎት ከሚያቀርቡ በቀር በሰበር ሰሚ ችሎቱ የሚስተናገድ አይደለም በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡

ተጠሪ ይህን ተከትሎ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት በመ.ቁ 0111919 አቤቱታ አቅርበው ችሎቱም አመልካች አስተያየት እንዲሰጡበት ካደረገ በኋላ በቀን 15/2/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት አመልካች ቀጠሮውን አክብሮ ቀርቦ ያልተከራከረው በበቂ ምክንያት በመሆኑ ሰበር ሰሚ ችሎቱ ክርክሩን በሌለበት ቀጥሎ በመ.ቁ 0329067 ጥር 27 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተነስቶ ክርክሩ ተጠሪ ባለበት ሊቀጥል ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በመ.ቁ 0329067 ክርክሩን ተጠሪ ባሉበት ቀጥሎ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው ሲል አጽንቶታል፡፡

አመልካች ጥቅምት 02 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይህን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ሲሆን ይዘቱም፦ በሌለሁበት የተሰጠ ውሳኔ ይነሳልኝ በሚል የሚቀርብን አቤቱታ ተቀብሎ ውሳኔ መስጠት ያለበት ውሳኔውን የሰጠው ፍርድ ቤት ብቻ ነው፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት ያለው ስልጣን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ካለው ስልጣን በታች ነው፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የካቲት 28 ቀን 2015 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ ቀደም ሲል ጥር 27 ቀን 2014 ዓ.ም ሰጥቶት የነበረውን ፍርድ ሊቀይር የቻለው ቀደም ሲል ተጠሪ በሌሉበት ተሰጥቶ የነበረውን ውሳኔ በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ መደበኛ ችሎት ታይቶ የተሻረ መሆኑን ተከትሎ ነው፤ ስለሆነም በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤተታ ተመርምሮ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪ በሌሉበት የሰጠው ፍርድ እንዲነሳላቸው ያቀረቡትን አቤቱታ ለይግባኝ ሰሚው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንዲቀርብ የሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ቁጥ 78 ጋር አገናዝቦ ለመመርመር ሲባል በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2/4(ለ) እና ቁጥር 28(3) እና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 7(3) መሠረት ተጠሪ ቀርበው መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ተጠሪ የፍርድ ቤቱን መጥሪያ ለመቀበል ፈቃደኛ እንዳልሆኑ በቃለመሐላ ስለተረጋገጠ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸውን ይመስላል፡፡ ይህ ችሎትም ያስቀርባል ሲባል የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ እንደቻልነው ተጠሪ በሌሉበት ጉዳያቸውን አይቶ ውሳኔ የሰጠው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መሆኑን፤ ተጠሪም በሌሉበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ ተነስቶ መልስ እንዲሰጡ ተደርጎ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ እንዲሰጥላቸው አቤቱታ ያቀረቡ መሆኑን፤ አቤቱታው የቀረበለት ሰበር ሰሚ ችሎቱም የተጠሪን መልስ የመስጠት መብት በመንፈግ ችሎቱ ውሳኔ የሰጠ ቢሆንም ችሎቱ ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመርመር እና የመመዘን ስልጣን ስለሌለው ተጠሪ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መደበኛው ችሎት ከሚያቀርቡ በቀር በሰበር ሰሚ ችሎቱ የሚስተናገድ አይደለም በማለት ውድቅ እንዳደረገው፤ ይህን ተከትሎ ተጠሪ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት አቤቱታ አቅርበው አመልካች በጉዳዩ ላይ አስተያየት እንዲሰጡበት ካደረገ በኋላ ተጠሪ ቀጠሮውን አክብሮ ቀርቦ ያልተከራከረው በበቂ ምክንያት ስለሆነ ሰበር ሰሚ ችሎቱ ክርክሩን ተጠሪ በሌለበት ቀጥሎ የሰጠው ውሳኔ ተነስቶ ክርክሩ ተጠሪ ባለበት ሊቀጥል ይገባል በማለት ውሳኔ እንደሰጠ፤ ከዚህ ውሳኔ በኋላ ደግሞ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪ ባሉበት ክርክሩን ቀጥሎ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው ሲል ያጸናው መሆኑን ነው፡፡

በመሠረቱ አንድ ተከሳሽ በክርክሩ ላይ ቀርቦ መልስ ሳይሰጥ ወይም ተገቢውን መከራከሪያ ሳያቀርብ በመቅረቱ በሌለበት አንድ ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ የተሰጠ ሲሆን ውሳኔው ወይም ትዕዛዙ መሰጠቱን በተረዳው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ቀርቦ ትዕዛዙ ወይም ውሳኔው እንዲነሳለት ሊያመለክት እንደሚችል፤ ተከሳሹ ይህን ማመልከቻ በሚያቀርብበት ጊዜ የጥሪው ትዕዛዝ በሚገባ ያልደረሰው መሆኑን ወይም ክርክሩ ሊሰማ በተቀጠረበት ቀን ቀርቦ መከራከሪያውን ያላሰማው ወይም መልስ ያልሰጠው በበቂ ምክንያት መሆኑን ፍርድ ቤቱ የተረዳ እንደሆነ የተከሳሹ አቤቱታ ላንደኛው ወገን ተከራካሪ እንዲደርሰው ካደረገ እና ተገቢውን ኪሣራ ወይም መቀጮ እንዲከፍል ካደረገ በኋላ ትዕዛዙን ወይም ብይኑን በማንሳት ክርክሩ እንዲገና የሚሰማበትን ቀነ ቀጠሮ እንደሚሰጥ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 78(1)(2) ላይ ተመልቷል፡፡ በዚህ አግባብ የሚቀርበው አቤቱታም ውሳኔውን በሰጠው ፍርድ ቤት የሚስተናገድ መሆኑን ከድንጋጌው ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ በሌሉበት ጉዳያቸውን አይቶ ውሳኔ የሰጠው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመሆኑ ተጠሪ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 78 መሠረት አቤቱታ ያቀረቡትም ለዚሁ ሰበር ሰሚ ችሎት ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተጠሪን አቤቱታ ውድቅ ያደረገው የተጠሪን መልስ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የመስጠት መብት የነፈገው እና የመጨረሻ ውሳኔ የሰጠው ይህ ችሎት ቢሆንም ችሎቱ ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመርመር እና የመመዘን ስልጣን ስለሌለው ተጠሪ አለኝ የሚሉትን መልስ የመስጠት መብት ጥያቄ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መደበኛው ችሎት ከሚያቀርብ በቀር በሰበር ሰሚ ችሎቱ የሚስተናገድ አይደለም በማለት ነው፡፡

በእርግጥ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግስት አንቀጽ 80/3(ለ) እና በተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ መሠረት ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ስልጣን መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበትን የመጨረሻ ውሳኔ ማረም እንጂ ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን አልተሰጠውም፡፡ ሆኖም ሰበር ሰሚ ችሎቱ በያዘው መዝገብ ላይ ከክርክር አመራር ጋር በተያያዘ የሚነሱ አቤቱዎችን የመምራት ሃላፊነት አለበት፡፡ ስለሆነም በያዘው መዝገብ ላይ ከክርክር አመራር ጋር በተያያዘ የሚነሱ አቤቱታዎችን ፍሬነገርን የመመርመር እና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን አልተሰጠኝም በማለት ውድቅ ሊያደርጋቸው አይገባም፡፡ በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪ መልስ የማቅረብ መብታቸው ታልፎ የተሰጠው ውሳኔ እንዲነሳላቸው ያቀረቡትን አቤቱታ ራሱ አይቶ መወሰን ሲገባው ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት አቤቱታቸውን ያቅርቡ በማለት የሰጠው ውሳኔ፤ በመቀጠልም ተጠሪ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት አቤቱታ አቅርበው የተሰጠውን ውሳኔ መሠረት በማድረግ ክርክሩን ተጠሪ ባሉበት ቀጥሎ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን ውሳኔ በማጽናት የሰጠው ውሳኔ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2/4(ለ) ላይ እንደተገለጸው ሕግን አላግባብ በመተርጎም የተሰጠ እና መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪ መልስ የማቅረብ መብታቸው ታልፎ የተሰጠው ውሳኔ እንዲነሳላቸው ያቀረቡትን አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 78 መሠረት አከራክሮ ተገቢ ነው ያለውን ብይን እንዲሰጥበት ማድረግ ሥነ ሥርዓታዊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 0329067 መጋቢት 27 ቀን 2014 ዓ.ም እና የካቲት 28 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 111919 ጥቅምት 15 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 9/1(ለ) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገጸው መሠረት ተጠሪ መልስ የማቅረብ መብታቸው ታልፎ የተሰጠው ውሳኔ እንዲነሳላቸው ያቀረቡትን አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 78 መሠረት አከራክሮ ተገቢ ነው ያለውን ብይን እንዲሰጥበት በማለት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 9/2(ለ) መሠረት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡

- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፍ/ደ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ሰ/መ/ቁ ፡- 245488

ጥቅምት 06 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ብርሃኑ መንግስቱ

ማርታ ተካ

አመልካች፡- አቶ ሁሴን አደም -ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አቤራ ከሲሳ -ቀረቡ

**መዝገቡ በክረምት ስራ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በኮንትራት የያዘውን ይዞታዬን አለቅም ያለኝ በመሆኑ በፍርድ ኃይል እንዲለቅልኝ ይወሰንልኝ በሚል በአሁን አመልካች ከሣሽነት በተጠሪ ተከሣሽነት በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት የሀላባ ልዩ ዞን የዌራ ዲጆ ወረዳ ፍርድ ቤት ቀርቦ በነበረ የገጠር መሬት ይዞታ ክርክር መነሻነት የወረዳ ፍርድ ቤቱ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ.ቁ 5 መሰረት የአመልካችን ክስ ውድቅ በማድረግ በመ/ቁ 03469 በቀን 01/02/2015 ዓ.ም የሰጠው ብይን በየደረጃው ባሉት ፍርድ ቤቶች የፀና በመሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ላይ የተፈፀመ የህግ ስህተት ይታረምልኝ በማለት አመልካች የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

በስር ፍርድ ቤት ቀርቦ የነበረው ክስ የሚያመለክተው አዋሣኞቹ በክሱ የተጠቀሰውን አራት ጥማድ መሬቴን ተጠሪ ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2000 ዓ.ም በኮንትራት አርሶ ሲጠቀምበት ከቆየ በኃላ ከሰጠሁት ዓመታት አሳልፎ በጉልበት ይዞ ሊለቅልኝ ፈቃደኛ ስላልሆነ የተጠቀመበትን የመሬት አበል እና ኪሳራ የመጠየቅ መብቴ ተጠብቆ መሬቴን እንዲለቅልኝ ይወሰንልኝ ሲሉ ክስ አቅርበዋል፡፡

የአሁኑ ተጠሪም በሰጡት መልስ አመልካች በመ/ቁ 01326 ክስ አቅርበው በቀን 21/10/2008ዓ.ም ክሳቸው ውድቅ በማድረግ ከተወሰነ በኃላ በድጋሚ ያቀረቡት ክስ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ.ቁ 5 መሰረት አስቀድሞ በፍርድ ባለቀ ጉዳይ በድጋሚ የቐረበ ክስ ነው የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አንስተዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም በተነሳው መቃወሚያ ላይ ግራቀችን ካከራከረ በኃላ ተጠሪ ከመልሱ ጋር በሰነድ ማስረጃነት አያይዞ ባቀረበው በመ/ቁ 01326 አመልካች በዚሁ መሬት ላይ

ከተጠሪ ጋር ተከራክረው ክሳቸው ውድቅ በማድረግ የተወሰነ መሆኑ ስለሚያሳይ የአመልካች ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ.ቁ 5 መሰረት አስቀድሞ ውሳኔ ባገኘ ጉዳይ በድጋሚ ያቀረቡት ክስ ነው በማለት ክሳቸውን ውድቅ በማድረግ በመ/ቁ 03469፤ በቀን 01/2/2015ዓ.ም ብይን ሰጥቷል፡፡

አመልካች ይህንኑ ብይን በመቃወም ለሀላባ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ በቀን 12577 በቀን 29/03/15ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ ይግባኙን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ.ቁጥር 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

እንዲሁም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ይግባኝም ፍርድ ቤቱ ይግባኙን ውድቅ በማድረግ በመ/ቁ 78235 በቀን 02/06/2015 ዓ.ም ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ በመቀጠል መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካች ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታቸው አቅርበው የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም ሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ብይን/ትእዛዝ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ በመ/ቁ 78296፤በቀን 30/6/2015ዓ.ም ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በስር ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ ሲሉ መጋቢት 07 ቀን 2015 ዓ.ም. ጽፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይዘቱም በአጭሩ፡- አመልካች አስቀድሞ በተጠሪ ላይ ያቀረብኩት ክስ ሁከት ይወገድልኝ በሚል አሁን ያቀረብኩት ደግሞ ይዞታዬ ይልቀቅልኝ የሚል ሆኖ እያለ የሁለቱ የሕግም ሆነ የፍሬነገር ክርክር ጭብጥ የተለያየ ሆኖ እያለና መሬቱ በማን ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ ከሚመለከተው አካል ሳይጣራ በድጋሚ የቀረበ ክስ ነው

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ተብሎ ክሴ ውድቅ መደረጉ የስር ፍርድ ቤቶች መሰረታዊ የሕግ ስህተት የፈፀሙ በመሆኑ ውሳኔዎች ተሽረው ወደ ዋናው ክርክር ገብተው ማስረጃ ሰምተው እንዲወስኑ ሊመለስ ይገባል በሚል ነው፡፡

የሠበር አቤቱታው ተመርምሮ የአመልካች ክስ መሬት ይልቀቀልኝ ዳኝነት መሆኑ እና ቀደም ሲል የተደረገው ክርክር የሁከት ይወገድልኝ ክስን መነሻ ያደረገ ውሳኔ ከመሆኑ አኳያ ክሱ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው መባሉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ.ቁ 5(1) እና በሰ/መ/ቁ 168195 እና በሌሎች መዝገቦች ላይ ከሰጠው አስገዳጅ ትርጉም አንጻር ተመሳሳይ ጭብጥ የሚነሳበት ነው ተብሎ መወሰኑ ህጋዊነቱን ለማጣራት ሲባል ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪም በቀን 04/12/2015 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት መልስ ይዘቱ የአሁን አመልካች በቀድሞ ሀላባ ልዩ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 01376 ሐምሌ ወር 2007 ዓ.ም በተጠሪ ላይ የሁከት ይወገድልኝ ክስ አቅርቦ ጉዳዩን በተመለከተው ፍርድ ቤት በማስረጃ ተረጋግጦ የተፈጠረ ሁከት የለም ብሎ ወስኗል፡፡ ይህ ውሳኔ በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች አልተሻረም፡፡ ነገር ግን አመልካች ሚስቴ ሞታና እኔ ታምሜ

ይግባኝ አላልኩም በማለት ያቀረበው ቅሬታ በህግ ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ አመልካች በሁለቱም መዝገቦች ላይ የጠየቀው ዳኝነት መሬቱን ለመረከብ በመሆኑ የክርክር ጭብጡ ተመሳሳይ ነው፤አመልካች የመጀመሪያውን ክስ በ2007 ዓ.ም መስርቶ ከ7 ዓመት በኋላ ክስ ያቀረበ ሲሆን ተጠሪ በመሬቱ ቀደም ሲል ቤት ሰርቼና አትክልቶችን አልምቼ ባለሁበት የክርክሩ መነሻ ጉዳይ አንድ በመሆኑ በሁለቱም ጉዳዮች ተጠሪ መሬቱ ሊለቅ ይገባል ወይም አይገባም የሚል ተመሳሳይ የክርክር ጭብጥ ያለው መሆኑን፤ ከሳሽ አንዴ የእኩል አራሽ ሆኜ መሬቱ ሰጥቼ በሌላ ጊዜ ደግሞ መሬቱን ለ3 ዓመት ኮንትራት ሰጥቼለሁ እያለ የዳኝነት ጥያቄው ሁከት ይወገድለኝ በሚል እና የመፋለም ክስ በሚል ማቅረቡ ተገቢነት የለውም፡፡ በመሆኑም በሁለቱም የሚጠይቀው ዳኝነት መሬት ያስረክበኝ የሚል በመሆኑ በቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መነሻ ክርክሩ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው በሚል በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ብይን ተገቢ ነው በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር በቀን 17/12/2015 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን በበኩላችን የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ብይን እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

የፍትሃ ብሄር ስነ ስርዓት ህጉ ክርክሮች መቋጫ ይኖራቸው ዘንድ ከዘረጋው ሥርዓት አንዱ በአንቀፅ 5 ሥር የተደነገገው የመጨረሻ ፍርድ ያገኙ ጉዳዮችን የተመለከተው ድንጋጌ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 ስር እንደተደነገገው አንድ ጉዳይ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው ለማለት መረጋገጥ ያላባቸው ሁኔታዎች ቀደም ሲል ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ የነበሩ ጉዳዮች በድጋሚ በቀረበው ክስም ላይ በቀጥታ በፍሬ ነገር ጭብጥ ሆነው መቅረባቸው፣ ቀደም ሲል የነበረውን ክርክር አሁን በክርክር ተሣታፊ በሆኑ ወገኖች ወይም ከእነሱ መብት በተላለፈላቸው ወገኖች መሆኑንና እነዚህ ጉዳዮች ቀደም ሲል በተካሄደው ሙግት የመጨረሻ ፍርድ ያረፈባቸው መሆኑን ይመለከታል፡፡ ከሕጉ ይዘት መገንዘብ እንደሚቻለው ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ የሚለው ሐረግ በመጀመሪያው ክርክር ላይ ከአንደኛው ወገን ተጠይቆ በሌላኛው ወገን የተካደ ወይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የታመነና በዚሁ ላይ የፍርድ ውሣኔ ያረፈበት የክርክር ነጥብ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም በቀረበው ክስ በቀድሞው ክርክር ተሣታፊ የነበሩ ወገኖች ወይም ከእነሱ መብት በተላለፈላቸው ወገኖች መካከል የሚካሄድ መሆን አለመሆኑ፣ በሁለተኛው ክስ የቀረበዉ የፍሬ ነገር ጉዳይና ጭብጥ ከመጀመሪያው ጋር ተመሣሣይ መሆን አለመሆኑና የመጨረሻ ፍርድ ያረፈበት መሆን አለመሆኑ ተጣርቶ ጉዳዩ የመጨረሻ ፍርድ ያገኘ መሆኑ ከተረጋገጠ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ክሱ ውድቅ እንደሚሆን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 5/1/ ድንጋጌ መረዳት የሚቻል ነው፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5/2/ ድንጋጌ በግልጽ ሲታይም በቀድሞው ክርክር ላይ የማስረጃ ወይም መየከላከያ ወይም የመቃወሚያ መሰረት መሆን ይገባቸው ነበር ወይም ለመሆን ይችሉ ነበር

የሚባሉት ነገሮችና ምክንያቶች ሁሉ ለሥረ ነገሩ መሰረት በመሆን በቀድሞው ውሳኔ ጋር ተቀላቅለው እንዳለቁ የሚቆጠሩ ናቸው በማለት አስገዳጅነት ባለው መልኩ ድንግጓል፡፡ እንዲሁም በቀድሞው ክርክርና ሙግት ላይ በግልጽ ዳኝነት ተጠይቆበት ጥያቄው ተቀባይነትን ሳያገኝ የታለፈ እንደሆነ የተጠየቀው ዳኝነት እንደተከለከለ እንደሚቆጠር የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 (3) ድንጋጌ በግልጽ አስቀምጧል፡፡ በአጠቃላይ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 ድንጋጌ ሲታይ በቀዳሚው ክርክር የተያዘው ጭብጥና የፍሬ ነገር ክርክር ተመሳሳይ መሆኑ የተከራካሪ ወገኖች አንድነት ብቻ ሳይሆን በጉዳዩ ላይ ከላይ የተመለከቱት መመዘኛዎች በተሟሉበት ሁኔታ የመጨረሻ ፍርድ የተሰጠ መሆኑ ከተረጋገጠ በጉዳዩ ላይ አስቀድሞ የመጨረሻ ፍርድ የተሰጠበት በመሆኑ ድጋሚ ክስ የሚቀርብበት አግባብ የሌለ መሆኑን ያስረዳል፡፡ ይህም ክርክሮች በአንድ ጊዜ ተጠቃልልው ጊዜን፣ ጉልበትንና ወጪን ቆጣቢ በሆነ መልኩ እንዲቀርቡ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

በማድረግ የተከራካሪ ወገኖችን እንግልት ለማስቀረት ተብሎ የተቀረፀ ስነ ስርዓታዊ ድንጋጌ እንደሆነ ተደርጎም ይወሰዳል፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች እና ተጠሪ የሚከራከሩበት የገጠር መሬት ይዞታ ከዚህ ቀደም አመልካች በመ.ቁ 013726 ይህንኑ መሬት ተጠሪ በኮንትራት አርሶ ለመጠቀም ወስዶ ለመመለስ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ሁከት ይወገድልኝ በሚል ክስ አቅርበው በግራቀኙ መካከል ክርክር ያስነሳው መሬት ባለመብት ማን ነው የሚለው በጭብጥነት ተይዞ ክርክር ተደርጎበት አመልካች ክርክር ያስነሳው ይዞታ ባለቤት ወይም ባለመብት መሆኑን አላረጋገጡም፤ በተጠሪ በኩል ምንም እንኳ ይዞታው በስማቸው የተሰጠ የይዞታ ማረጋገጫ የሌላቸው ቢሆንም ይዞታው ለረጅም አመታት በእጃቸው ተይዞ የቆየ በመሆኑ ከአመልካች የተሻለ በይዞታው ላይ መብት ያላቸው በመሆኑ ተጠሪ የፈጠሩት ሁከት የለም በሚል መወሰኑ ተመልክተናል፡፡

አመልካች አስቀድመው በመ/ቁ 01326 ያቀረቡት የሁከት ይወገድልኝ ክስ ውድቅ በማድረግ ሲወሰን አመልካች የይዞታው ባለመብት ስለመሆናቸው አለመረጋገጡ እንዲሁም ተጠሪ በይዞታው ላይ የተሻለ መብት ያላቸው መሆኑን ጠቅሶ ተጠሪ የፈጠሩት ሁከት የለም በሚል መሆኑን ውሳኔው ያሳያል፡፡ አመልካች በዚሁ ይዞታ ላይ ባለመብት ስለመሆናቸው አላረጋገጡም እንዲሁም ተጠሪ በይዞታው ላይ የተሻለ መብት አላቸው ተብሎ አስቀድሞ የተሰጠው ውሳኔ ፀንቶ ያለ መሆኑ በግራቀኙ በኩል የተካደ አይደለም፡፡

አመልካች ለዚህ ሰበር መቅረብ ምክንያት የሆነው በስር ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 03469 ላይ ባቀረቡት ክስ የሚጠይቁት ዳኝነት ይህንኑ መሬት ተጠሪ በኮንትራት ወስደው ሲጠቀሙ ቆይተው ሊያስረክቡኝ ስላቻሉ ለቀው ያስረክቡኝ የሚል ነው፡፡ ከዚህም መረዳት እንደሚቻለው አመልካች አስቀድሞ ያቀረቡት ክስ ምንም እንኳ ሁከት ይወገድልኝ በሚል የቀረበ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ በይዞታው ላይ የተሻለ መብት ያለው ማን ነው በሚለው ጭብጥ ላይም ጭምር ክርክር ተደርጎበት አመልካች በዚሁ ይዞታ መሬት ላይ መብት ያለው ስለመሆኑ አላረጋገጠም፤ተጠሪ ከአመልካች

የተሻለ መብት አለው በሚል ተወስኖ እያለና ውሳኔው ፀንቶ እያለ እንደአዲስ ክርክር ያስነሳው ይዞታ አመልካች ባለመብት በመሆኔ ተጠሪ ለቆ ያስረክበኝ በሚል ይዞታን በማስለቀቅ ለመረከብ ያቀረቡት ክስ በመ/ቁ 01376 በነበረው የሁከት ይወገድልኝ ክርክር ጋር የይዞታ ባለመብትነት ክርክርም ተደርጎበት ውሳኔ ባገኘ ጉዳይ በድጋሚ የቀረበ ክስ በመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 ድንጋጌዎች አንፃር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ሁከቱ ተወግዶ ይዞታ እንዲለቅ ክስ ቀርቦ ፍርድ ከተሰጠ በኃላ

በድጋሚ ይዞታ ይልቀቅልኝ በሚል የሚቀርብ ክስ ዳኝነት በተሰጠበት ጉዳይ ላይ በድጋሚ የቀረበ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ.ቁ 5(1)፤ 244(2)ለ መሰረት ተቀባይነት እንደማይኖረው በሰ/መ/ቁ 138062 ላይ ገዢ የሕግ ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡

በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤት በድጋሚ የቀረበው ክስ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 5፣ 244(ለ) እና 245 መሰረት ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ያሳለፈው ብይንና በየደረጃው ቅሬታ የቀረበላቸው ፍርድ ቤቶች ቅሬታውን አለመቀበላቸው ህጉንና ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠውን ትርጉም መሠረት ያደረገ መሆኑን ስለሚያሳይ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4) እና 10(1/ሐ/ እና /መ) ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች አንፃር ሲታይ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በስሩ ያሉት ፍርድ ቤቶች የሰጡት ብይን/ትእዛዝ በማጽናት በመዝገብ ቁጥር 78296፤የካቲት 30 ቀን 2015 ዓ/ም የሰጠው ትእዛዝ በሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1)(ሀ) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
3. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ. 245552

ጥቅምት 08 ቀን 2017 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

ሰናይት አድነው

ሀፊዝ አባጆማል

**አመልካች-**፡- ሕብረት ኢንሹራንስ አ.ማ ነ/ፈጅ ሶስና ሙሉ

**ተጠሪ**፡- አዋሽ ኢንሹራንስ ነ.ፈጅ ሠላም አበበ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ፍርድ</u>**

ጉዳዩ የኢንሹራንስ ዉል አፈፃፀምን የሚመለከት ሲሆን፣ ክርክሩ በተጀመረበት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ በአመልካች እና በዚህ ችሎት የክርክሩ ተሳታፊ ባልሆኑት በስር 1ኛ ተከሳሽ ላይ ባቀረበዉ ክስ ተጠሪ የመድን ሽፋን የሰጠዉ እና ንብረትነቱ የወ/ሮ ህልዉና ነስሩ የሆነዉን ተሽከርካሪ ንብረትነቱ የስር 1ኛ ተከሳሽ ሆኖ በአመልካች የመድን ሽፋን በተሰጠዉ ተሽከርካሪ ተገጭቶ ጉዳት ስለደረሰበት አመልካች ባለበት ከመድን ዉል የመነጨ ግዴታ መሠረት በአጠቃላይ ብር 52,443.63 ወጪ በማድረግ ያስጠገነዉ መሆኑን ጠቅሶ ከዚህ ዉስጥ የአደጋ መዋጮ እና የቅሪት አካል ተቀናሽ ተደርጎ ብር 49,885.20 አመልካች እንዲተካለት የጠየቀዉን ዳኝነት መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡

አመልካች በሰጠዉ መልስ ጉዳት የደረሰበት ተሽከርካሪ ጉዳቱ በደረሰበት ወቅት የነበረዉ የገበያ ዋጋ ብር 1,449,999.99 ሲሆን የመድን ሽፋን በሚሰጥበት ወቅት የገበያ ዋጋዉ ብር 1,300,000.00 መሆኑን፣ ይህም የመኪናዉ ዋጋ የመድን ሽፋን ከተሰጠዉ የገበያ ዋጋ ብልጫ ያለዉ መሆኑን የሚያሳይ መሆኑን፣ በአደጋዉ ወቅት ያለዉ የገበያ ዋጋ ሽፋን ከተገባለት የገበያ ዋጋ ከፍ ያለ እንደሆነ ንብረቱ ዝቅተኛ ሽፋን

(under ensured) በመሆኑ ልዩነት ለፈጠረዉ የንብረቱ ዋጋ መድን ገቢዉ ራሱ ሽፋን እንደሰጠዉ ስለሚቆጠር በልዩነቱ ላይ ወጪዉን የመተካት ግዴታ ያለበት መሆኑን፣ በዚህም መሠረት ተጠሪ የመድን ሽፋን የሰጠዉ ተሽከርካሪ ሽፋን ከተገባለት የገበያ ዋጋ እና በአደጋዉ ወቅት ካለዉ የገበያ ዋጋ ጋር ተነጻፅሮ ሂሳቡ ሲሰራ ተጠሪ ከጠየቁት ገንዘብ ብር 49,885.33 ዉስጥ ብር 5,487.38 ቀንሶ ብር 44,397.94 ብቻ መክፈል ሲገባዉ ይህን ሳይቀንስ ለከፈለዉ ገንዘብ አመልካች ኃላፊነት የሌለበት መሆኑን ጠቅሶ ብር 44,397.94 ለመክፈል ፈቃደኛ መሆኑን በመግለጽ ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር ከሰማ በኋላ ተጠሪ ጉዳት ለደረሰበት ተሽከርካሪ መድን ሲገባ 1,300,000.00 ቢሆንም መኪናዉን ያስጠገነበት ዋጋ ከዚህ በታች መሆኑን ጠቅሶ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበዉን ክርክር ዉድቅ በማድረግ አመልካች ለጥገና የወጣዉን ወጪ ብር 49,885.33 ከስር 1ኛ ተከሳሽ ጋር በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን፣ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ በበኩሉ መዝገቡን አስቀርቦ የግራ ቀኝ ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች ለክርክሩ መሠረት ያደረገዉ የንግድ ህጉ አንቀጽ 679 እና ተከታዮቹ ድንጋጌ የሚያገለግለዉ መድን በተገባለት ተሽከርካሪ ላይ ጠቅላላ ዉድመት ከደረሰበት ነዉ በማለት የስር ፍርድ ቤቱን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም በዚሁ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካች ሚያዝያ 10 ቀን 2015 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በንግድ ህጉ አንቀጽ 679 ላይ የተመለከተዉ ድንጋጌ የሚያስረዳዉ በአደጋዉ ወቅት በተሽከርካሪዉ የገበያ ዋጋ ላይ ጭማሪ ካለ መድን ገቢዉ ልዩነቱን እራሱ የሚሸፍን መሆኑን እንጂ ለጠቅላላ ዉድመት ነዉ? ወይስ ለከፊል ጉዳት ነዉ? በሚል ለይቶ ባላስቀመጠበት ሁኔታ የመድን ሽፋን በተሰጠበት ወቅት የነበረዉን የተሽከርካሪዉን ዋጋ ጉዳት በደረሰበት ወቅት ከነበረዉ ዋጋ ቀንሶ በልዩነቱ ልክ ስሌቱ በአማካይ ተሰርቶ የሚመጣዉ ብር 5,487.38 መቀነስ ሲገባዉ ሳይቀነስ መታለፉ መሠረታዊ የህግ ስህተት መሆኑን ጠቅሶ ታርሞ እንዲወሰንለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

የሰበር አቤቱታዉ በሰበር ችሎት ተመርምሮም የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካችን ክርክር ዉድቅ ያገረጉበት አግባብ የንግድ ህጉን አንቀጽ 679 ድንጋጌ ትክክለኛ ይዘት ያገናዘበ መሆን አለመሆኑ ግራ ቀኝ በተገኙበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል ተብሏል፡፡ በዚህም መሠረት ተጠሪ የካቲት 11 ቀን 2016 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበዉ መልስ የንግድ ህጉ አንቀጽ 679 መድን የተገባለት ተሽከርካሪ ዋጋ ጭማሪ አረቦን በተከፈለበት ጊዜ ከነበረዉ የገበያ ዋጋ የጨመረ እንደሆነ አረቦን እስከተከፈለበት ድረስ ብቻ መድን ሰጪዉ ካሳ ሊከፍል የሚገባዉ መሆኑንና ቀሪዉን መድን ገቢዉ እንዲሸፍን ታስቦ የተደነገገ በመሆኑ አረቦን ከተከፈለበት ዋጋ በላይ ላልደረሰ ጉዳት የንብረቱን ልዩ ልዩ ክፍሎች በዋጋ ጭማሪዉ ልዩነት እየተሰላ መድን ገቢዉ አረቦን እስከከፈለበት መጠን እንዳይከፈለዉ የሚያደርግ በመሆኑ የአመልካች ክርክር ተቀባይነት የለዉም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች የካቲት 27 ቀን 2016 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል፣ ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታዉን ለማስቀረብ የተያዘዉን ጭብጥ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል። እንደመረመረዉም አመልካች ከስር ጀምሮ የሚከራከረዉ የመድን ሽፋን ሲሰጥ የነበረዉ የተሽከርካሪዉ ዋጋ

ጉዳቱ በደረሰበት ወቅት ከነበረዉ ዋጋ ያነሰ በመሆኑ ልዩነቱን የመክፈል የመድን ገቢዉ በመሆኑ አመልካች በዚያዉ ልክ ኃላፊነት የሌለበት መሆኑን በመጥቀስ ሲሆን፣ ተጠሪ በበኩሉ ወጪዉ አረቦን ከተከፈለበት የተሽከርካሪዉ ዋጋ በላይ እስካልሆነ ድረስ አመልካች በወጣዉ ወጪ ልክ የመካስ ኃላፊነት አለበት የሚል ይዘት ያለዉ ምክንያት በመጥቀስ ይከራከራል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበዉን ክርክር ዉድቅ ያደረገዉ ለጥገና የወጣዉ ወጪ በመድን ሽፋኑ ወቅት ከነበረዉ የመኪናዉ ዋጋ በታች መሆኑን በመጥቀስ ሲሆን፣ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተዉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በበኩሉ የንግድ ህጉ አንቀጽ 679 እና ተከታዮቹ ተፈፃሚ የሚሆኑት ጠቅላላ ዉድመት የደረሰ እንደሆነ ነዉ የሚል ምክንያት በመጥቀስ የስር ፍርድ ቤቱን ዉሳኔ አጽንቶታል፡፡

በንግድ ሕጉ አንቀጽ 679 መሠረት ኢንሹራንስ የገባው ዕቃ ጉዳት በደረሰበት ቀን ያወጣ የነበረው ዋጋ ኢንሹራንስ ከገባበት ዋጋ በልጦ ሲገኝ በልጦ ለሚገኘው ዋጋ ኢንሹራንስ ገቢው ራሱ እንደኢንሹራንስ አድራጊ ተቆጥሮ ከጉዳቱ በመጠኑ በከፊል እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ ይሕም ውሉ በመጀመሪያ ሲመሰረት ወይም ውሉ በሚታደስበት ጊዜ ሊከሰት የሚችል ሲሆን መድን ገቢው ትክክለኛው የዕቃው ዋጋ ሳይሆን ዝቅ አድርጎ ሲያስመዘግበ ኃላፊነቱ ወደእርሱም የሚመጣበት ሁኔታ እንዳለ ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡ የመድን ሰጪ ኃላፊነቱ የሚመነጨው ከውል ሲሆን ለኃላፊነት መጠኑ መሠረት ደግሞ የእቃ ዋጋ እና መድን ገቢውን የሚያስከፍለው አረቦን ነው፡፡ የእቃ ዋጋ ዝቅ ከተደረገ ሕጉ ያላግባብ ዝቅ ከተደረገው ዋጋ በላይ ላለው አረቦን እንዳልተከፈለበት ታሳቢ በማድረግ ኃላፊነቱ ለመድን ሰጪው ሳይሆን ለዕቃው ባለቤት መድን ገቢው ስለመሆኑ በግልጽ አስቀምጧል፡፡ በዚህ ጊዜ መድን ሰጪው ሊከፍል የሚገባው የእቃው ትክክለኛ ዋጋ የመድን ውሉ ላይ ከተመለከተው ዋጋ እና የደረሰው ጉዳት በአማካይ ተሰልቶ በሚመጣው ውጤት መሆን ይገባዋል፡፡ መድን ገቢዉ እራሱ እንደ ኢንሹራንስ አድራጊ ተቆጥሮ ልዩነቱን ለመክፈል የሚገደደዉ የመድን ሽፋን በተሰጠዉ ተሽከርካሪ ላይ ጠቅላላ ጉዳት ከደረሰ ብቻ ነዉ የሚል የሚል በህጉ አልተመለከተም፡፡ ከላይ እንደተመለከተዉ የንግድ ህጉ አንቀጽ 679 አጠቃላይ ዓላማ መድን ገቢዉ ትክክለኛዉን የዕቃዉን ዋጋ ሳይሆን ዝቅ አድርጎ ያስመዘገበ እንደሆነ ኃላፊነቱ ወደ እርሱም እንዲመጣ ማድረግ ከመሆኑ አኳያም ሲታይ ድንጋጌዉ ተፈፃሚነት ሚኖረዉ ለጠቅላላ ዉድመት ብቻ ነዉ የሚለዉ መደምደሚያ የህጉን ትክክለኛ ይዘት ያገናዘበ ነዉ ለማለት አይቻልም፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች ያቀረበዉን ክርክር ዉድቅ በማድረግ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የጸናዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ ነዉ፡፡

ስሌቱን በተመለከተ አመልካች ባቀረበዉ መልስ የመድን ሽፋን ሲሰጥ የነበረዉ የተሽከርካሪዉ ዋጋ ብር 1,300,000.00 ÷ አደጋዉ ሲደርስ የነበረዉ ዋጋ 1,449,999.99*100% = 89% ሲቀነስ ቀሪዉ 11% መድን ገቢዉ መሸፈን ያለበት ሲሆን ይህ ተሽከርካሪዉን ለማስጠገን ከወጣ ወጪ ብር 49,885.33 ዉስጥ 11% ወደ ገንዘብ ሲቀየር ብር 5,487.38 መድን ገቢዉ ሊከፍል የሚገባዉ መሆኑን ነዉ፡፡ የዚህን ስሌት ትክክለኛነት አስመልክቶ የቀረበ ክርክር የለም፡፡ በመሆኑም ይህንኑ ከግምት ዉስጥ በማስገባት ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ዉሳኔ**

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 02640 ላይ ታህሳስ 06 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 300404 ላይ መጋቢት 26 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጡት ዉሳኔ ተሻሽሏል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

2. አመልካች ብር 5,487.38 ተቀንሶ አመልካች ብር 44,397.94 (አርባ አራት ሺህ ሦስት መቶ ዘጠና ሰባት ብር ከ94/100) እንዲከፍል ተወስኗል፡፡
3. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፍ/ደ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ.መ.ቁ.245575

ጥቅምት 06 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች፡…1. ብርሃኑ አመነዉ

2. በእዉቀት በላይ

3. ቀነዓ ቂጣታ

4. ብርሃኑ መንግስቱ

5. ማርታ ተካ

አመልካች፡ ……..ዳሽን ባንክ አ.ማ -ነገረፈጅ ደረጀ ሊዮ -ቀረቡ

ተጠሪ፡…………የአሶሳ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች መምሪያ -የቀረበ የለም

ይህ መዝገብ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ይህ የመኖሪያ ቤት ክርክር የተጀመረዉ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል በአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች የሥር ከሳሽ፣ የአሁን ተጠሪ የሥር ተከሳሽ ሆኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ አመልካች የቤንሻንጉል ጉሙዝ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.12334 በ05/07/2015 ዓ.ም የሰጠዉ ፍርድ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት በማመልከቱ ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ ከሳሽ በሥር ፍ/ቤት ባቀረበዉ የክስ አቤቱታ፡ ፈለማ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር በ9/6/2010 ዓ.ም በተጻፈ የብድር ዉል መሰረት በተወሰነ ጊዜ የሚከፈል ብድር

**ማስታወሻ፡** - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

ዉል ሃያ ሚሊዮን እና በብድር መክፈት ሂሳብ ብድር ዉል አስራ አንድ ሚሊዮን በድምሩ ብር ሰላሳ አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ከከሳሽ ተበድሮ ለገንዘቡ መክፈል ዋስትና ይሁን ዘንድ በብድር ዉሉ መሰረት ከሳሽ በመያዣነት ከያዛቸዉ የማህበሩ ንብረቶች ዉስጥ 1ኛ የሰሌዳ ቁጥር ኢት-03-59294 እና 2ኛ የሰሌዳ ቁጥሩ ኢት-03-57247 የሆነ ልዩ ተንቀሳቀሽ ክሬን መኪና በጨረታ መነሻ ዋጋ ሁለት ሚሊዮን አንድ መቶ ሺህ አራት መቶ ሰባ አራት ከ13 ሳንቲም ተከሳሽ ከማህበሩ የሚፈለግ የታክስ ዕዳ ለማስከፈል በሚል ግንቦት 5 ቀን 2014 ዓ.ም በጋዜጣ የግልጽ ጨረታ ሽያጭ ማስታወቂያ መዉጣት ለመሸጥ ወስኗል፡፡ በመሆኑም የባንኩ ዕዳ ተከፍሎ እስኪያልቅ ድረስ በመያዣ የተያዙ የማህበር ተሽከራካሪዎች እንዳይሸጡ እንዳይለወጡና ለሶስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ፣ ተሽከርካሪዉን አሳግደን በዕዳ የተመዘገበልን ሆኖ እዳዉ ሳይከፈለን የቅድሚያ መብት ባቋቋምንባቸዉ ንብረቶች ላይ የጨረታ ማስተወቂያ በማዉጣት በመሸጥ ብድሩ እንዲመለስ ለማድረግ ስለሆነ የወጣዉ ጨረታ እንዲሰረዝ እንዲወሰንልን፣ ንብረቶቹ በጨረታ እንዲሸጡ ከተባለ ግምቱ ዝቅተኛ ስለሆነ ድጋሚ በገለልተኛ ተገምቶ ለሐራጅ እንዲቀርብ፣ ገንዘቡም ቅዲሚያ ለከሳሽ እንዲከፍል እንዲወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ተከሳሽ በዚህ ክስ ላይ ባቀረበዉ ክርክር ጨረታ የወጠቸዉ ተሽከርካሪዎች የግብር ባለእዳ የሆነዉ ፈለማ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር በአሶሳ ዩኒቨርሲቲ ግብ ዉስጥ ሰራተኞችን ቀጥሮ ግንባታ በሚገነባበት ጊዜ ከሰራተኞቹ የቆርጦ የሰበሰባቸዉና ከተከፋይ ሒሳብ ላይ ተቀንሶ ለመንግስት ገቢ ማድረግ የሚገባዉን ታክስ [withholding tax] ለግል ጥቅሙ ያዋለ በመሆኑና ለመክፈልም ፈቃደኛ ባለመሆኑ የተከሳሽ መ/ቤት ከከሳሽ ይልቅ የቅድሚያ መብት ስላለዉ ጨረታዉ መዉጣቱ ተገቢ ነዉ በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በተከሳሽ የተነሳዉን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በብይን ዉድቅ በማድረግ፣ የሰዉ ምስክሮችን በመስማትና የሰነድ ማስረጃን በመመርመር በሰጠዉ ዉሳኔ ፈለማ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ከከሳሽ ገንዘብ ሲበደር ለክርክር መነሻ የሆኑትን ተሽከራካሪዎችን በመያዣ በማስያዝ መሆኑን በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠና በተከሳሽን ያልተካዳ ጉዳይ ነዉ፤ ይሁን እንጂ ይህ ማህበር ከሰራተኞች የሰበሰበዉን ከተከፋይ ሒሳብ ላይ ተቀንሶ የሚከፈል ታክስን [withholding tax] ለመንግስት ገቢ ያላደረገ በመሆኑ ተከሳሽ የማህበሩን ንብረት በሐረጅ ሽጦ የመንግስት የግብር ዕዳ ለማስከፈል የቀደሚነት መብት አለዉ የሚል ነዉ፤ በፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 39 (1) (2) እና ቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 142/2008 አንቀጽ 39 (1) (2) መሰረት በሚመለከተዉ አካል

ማንኛዉም ቀዳም ዋስትና የተሰጠበት መብት እንደተጠበቁ ሆነዉ በታክስ ሕግ መሰረት ታክስ ከፋይ መክፈል የሚገባዉ የመክፈል ጊዜዉ የደረሰ ታክስ ሙሉ በሙሉ ከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ ባለስልጣኑ በታክስ ከፋዩ ሀብት ላይ የቀደምትነት መብት እንዳለዉ ሁሉ የታክስ ከፋዩን ንብረት አስቀድሞ በመያዣ የያዙት ባንኮች በአዋጁ አንቀጽ 7 መሰረት የቀደምትነት መብት የሚኖራቸዉ ብድሩ ከመሰጠቱ በፊት ታክስ ከፋዩ የታክስ እዳ የሌለበት መሆኑን ባለስልጣኑ ሲያረጋግጥ ነዉ፡፡ ከዚህም በላይ ቀደም ሲል የማህበሩ ሰራተኞች የደመዉዝ ክፍያ ጥያቄ አቅርበዉ በማህበሩ ላይ አቅርበዉ የተወሰነላቸዉ ሲሆን አመልካች የቀደሚነት መብት አለኝ በማለት አቤቱታ በአፈጻጸም ላይ ያቀረበ ቢሆንም ጥያቄዉ ተቀባይነት ሳያገኘዉ ቀርቦ ተሸከርካሪዉ ተሸጦ የሚተርፍ ገንዘብ ካለ እንዲከፈላዉ መብት የተጠበቀለት በመሆኑ ገንዘቡ አስቀድሞ በሌላ ፍ/ቤት ለሌላ ወገን የተወሰነ መሆኑን ያሳያል፡፡ ተከሳሽ የግብር ከፋይ ንብረት የሆኑትን ክርክር የተነሳባቸዉን ተሸከርካሪዎችን በጨረታ ሸጦ የመንግስትን የግብር ዕዳ ለማስከፈል ተከሳሽ ከከሳሽ ይልቅ የቀዳሚነት መብት ያለዉ መሆኑ መብት ያለዉ መሆኑ ስለተረጋገጠ፣ ንብረቶቹ ተሸጦ የሚተርፍ ገንዘብ ካለ ለሌላ ወገን አስቀድሞ በሌላ ፍ/ቤት የተወሰነ በመሆኑ የከሳሽ ክስ ዉድቅ ነዉ በማለት ወስኗል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የቀረበለትን ይግባኝ መነሻ በማድረግ ግራ ቀኙን በማከራከር የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች ሚያዚያ 11 ቀን 2015 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ አመልካች እነዚህን ለጨረታ የቀረቡትን ንብረቶች በዋስትና በያዘበት የግብር አመት ዉስጥ ተበዳሪ ምንም ዓይነት የግብርም ሆነ ከማናቸዉም እዳና እገዳ እዳ መሆኑን አረጋግጦ ንብረቶቹን በዋስትና የያዘቸዉ መሆኑ የተረጋገጠ ሆኖ ሳለ፣ ተጠሪ ደግሞ ከግብር ከፋይ ማህበር የሚፈለገዉን ተሰብሳቢ ተቀናሽ ገንዘብ ያልከፈለ መሆኑን ቅቡልነት፣ ተገቢነት እና ሕጋዊነት ባለዉ የሰነድ ማስረጃ ባላስረዳበት ይህ ሰበር ችሎት በሰ.መ.ቁ.184757 ላይ ከሰጠዉ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶ ባለበት የሥር ፍ/ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡ የታክስ ዉሳኔ መግለጫ ተብሎ ነዉ የቀረበዉ ሰንጠረዥ ያለአባሪ የቀረበ በተጨማሪ ስልጣን ባለዉ ኃላፊ ተፈሪሞ ያልቀረበ ሆኖ ሳለ የሥር ፍ/ቤቶች የዚህ ማስረጃ ሕጋዊነት በሚገባ ማጣራት ሲገባቸዉ ይህን ሳይደርጉ የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡ የሥር ፍ/ቤት ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 33 መሰረት የቅድሚያ መብት የሚኖረዉ ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶች [withholding tax] ታክስ ብቻ ሆኖ ሳለ የሥር ፍ/ቤት ይህ መሆኑን ሳያጣራ የጡረታ መዋጮን

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ዉሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

በመደመር የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነዉ፡፡ አመልካች እነዚህ የብድር ማስመለሻ ንብረቶች ላይ የቅድሚያ መብት ያቋቋመ በመሆኑ ይህን መብቱን የሚያሳያጠዉ ነገር በሌለበት የሥር ፍ/ቤት በሌላ ፍ/ቤት ለሌሎች ተከራካሪ ወገኖች ተወስኗል በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ ይህ ሰበር ችሎት ከሰጠዉ አስገዳጅ ዉሳኔን ያላገናዘበ ነዉ፤ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ እንዲሻርልን በማለት አመልክቷል፡፡

ይህ ሰበር ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣አመልካች ከዉል የመነጨ የቀዳሚነት መብት ያነሳ ሲሆን ተጠሪ ደግሞ ከታክስ አስተዳደር ሕግ የመነጨ የቀዳሚነት መብት በማንሳት የተከራከረ በመሆኑ በእነዚህ ዓይነት ሁኔታ ይ ሰበር ችሎት በሰ.መ.ቁ.184757 እና በሌሎች መዛግብት ከሰጣቸዉ አስገዳጅ የህግ ትርጉም አንጻር ለመመርመር ሲባል የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ባዘዘዉ መሰረት በ9/7/2016 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት ባጭሩ፡ ተጠሪ በወቅቱ ያልተከፈለዉን ታክስ ለማስመለስ በግብር ከፋይ ንብረት ላይ በዚህ ንብረት ላይ ቅድሚያ ካቋቋሙ ሶስተኛ ወገኖች ይልቅ የቅድሚያ እንዳለዉ ይህ ሰበር ችሎት በሰ.መ.ቁ.184757 ላይ አስገዳጅ ዉሳኔ የሰጠ በመሆኑ እና በአዋጅ ቁጥር 983/2008 እና 143/2009 አንቀጽ 33 (1) (ሀ) እና መመሪያ ቁየጥር 6/2011 አግባብ በመሆኑ ጨረታዉ ሊቆም ስለማይገባዉ የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ የሚነቀርበት የህግ አግባብ የለም፡፡ ተጠሪ የጡረታ ግብርን ለመሰብሰብ ስልጣን እንዳለዉ በሥር ፍ/ቤት ማስረጃ ቀርቦ የተረጋገጠ ጉዳይ ነዉ፡፡ ተጠሪ ቀደም ሲል ከግብር ካፋዩ ገንዘብ ከሚጠይቁ ሰራተኞች ጋር ተከራክሮ የቅድሚያ መብት እንዳለዉ የተወሰነ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ ዉሳኔዉ እንዲጸናልን በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር መጋቢት 25 ቀን 2016 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር እና ለሰበር ቅሬታዉ መነሻ ከሆኑት የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ የአሁን አመልካች ንብረትነታቸዉ የፊለማ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና ለክርክር መነሻ የሆኑትን ተሽከራካሪዎች ማህበሩ ከአመልካች ባንክ ለተበደራዉ የብድር ገንዘብ ማስከፈያ ይሆን ዘንድ በመያዝ የያዛቸዉ መሆኑ ያላከራከረ ጉዳይ ነዉ፡፡ በሌላ በኩል የአሁን ተጠሪ ባቀረበዉ ክርክር ይህ ማህበር በየወሩ ከሰራተኞች ደመወዝ ማለትም ከተከፋይ ሒሳብ ላይ ተቀንሶ የሚከፈል ታክስን [withholding tax] ለመንግስት ገቢ ያላደረገ በመሆኑ፣ የአመልካች ባንክ በመያዣ የያዛቸዉ

ተሽከርካሪዎች በጨረታ ተሸጠዉ ገንዘቡ እንዲከፈለዉ የሐረጅ ማስታወቂያ ያወጣ መሆኑን መዝገቡ ያሳያል፡፡ ከዚህ አንጻር ግራ ቀኛቸዉ የሚከራከሩበት የማህበሩ ተሽከራካሪዎች ላይ አመልካች ከመያዣ ዉል የመነጨ መብት የጠየቀ ሲሆን፣ ተጠሪ ደግሞ ከታክስ አስተዳደር ሕግ የመነጨ መብት የጠየቀ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በመሆኑም በእነዚህ ንብረቶች ላይ የቀዳሚነት መብት ያለዉ ከመያዣ ዉል መብት ያለዉ አመልካች ነዉ ወይስ ከታክስ አስተዳደር ሕግ የመነጨ መብት ያለዉ ተጠሪ ነዉ? የሚለዉ ነጥብ ምላሽ የሚሻ ጉዳይ ነዉ፡፡

እንደሚታወቀዉ በፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 2 (31) ሥር ‹‹ታክስ›› ማለት በታክስ ሕጎች መሰረት የሚጣል ታክስ ሆኖ፣ ከሚጨምራቸዉ ታክስ መካከል አንዱ ‹‹በከፋዩ ተቀንሶ የሚቀር ታክስ›› [withholding tax] መሆኑን የድንጋጌዉ ንዑስ አንቀጽ (ሀ) ያመለክታል፡፡ በከፋዩ ተቀንሶ የሚቀር ታክስ መንግስት በክፍያ ላይ ከገቢዉ ከምንጩ ገቢዉ በተከፋዩ እጅ ሳይገባ የሚሰበስበዉ የገቢ ግብር ነዉ፡፡ ይህ ታክስ ክፍያዉ ለተከፋዩ ሳይፈጸም ከገቢዉ ምንጭ ላይ በከፋዩ ከሚሰበሰብባቸዉ ክፍያዎች መካከል አንዱ ለሰራተኞች የሚከፈል ደመወዝ ነዉ፡፡ አሠሪዉ ለሰራተኛዉ ደመወዝ ከመክፈሉ በፊት ይህን ታክስ ቀንሶ ለመንግስት የሚከፍል መሆኑን ነዉ፡፡ የዚህ ታክስ አሰባሰብ ደግሞ መንግስት ታክስ ስወራን ለማቀነስ እና ታክስ በጊዜ መሰብሰቡን ለማረጋገጥ እንደሚረዳዉ ይታመናል፡፡ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ የሚከፈል ታክስ (withholding tax) በተመለከተ የግብር ሰብሳቢዉን ባለስልጣን እና የሶስተኛ ወገን የቅድሚያ መብት በተመለከተ የአዋጁ አንቀጽ 33 (1) (ሀ) ድንጋጌ ሥር የተመለከተዉ የቅድሚያ መብት ተፈጻሚ ከሚሆንባቸዉ ክፍያዎች መካከል አንዱ ‹‹ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ የሚከፈል ታክስ›› መሆኑን የሚደነግግ ሲሆን፣ የዚህ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ (3) (ሀ) ደግሞ ይህ ታክስ ‹‹ከማንኛዉም ሰዉ ለሚፈለግ ማንኛዉም እዳ ወይም ኃላፊነት ማስፈጸሚያ ሊከበር እንደማይችል›› ያመለክታል፡፡ እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 39 (1) (2) መሰረት በሚመለከተዉ አካል የተመዘገበ ቀደሚ ዋስትና የተሰጠበት መብት እንደተጠበቀ ሆነዉ፣ በታክስ ሕግ መሰረት ታክስ ከፋዩ መክፈል የሚገባዉ የመክፈያ ጊዜዉ የደረሰ ታክስ በሙሉ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ ባለስልጣኑ በታክስ ከፋዩ ሀብት ላይ የቀደምትነት መብት እንደሚኖረዉ፣ ይህም መብት ባንኮች ዋስትና የተቀበሉባቸዉ የገንዘብ ጥያቄዎችና የተቀጣሪዎችን የደመወዝ የቅድሚያ መብት እንደሚጨምር፣ ሆኖም በአዋጁ አንቀጽ 33 (1) (ሀ) ከተመለከቱት ታክሶች ጋር በተገናኘ ተፈጻሚ እንዳማይሆን ይደነግጋል፡፡ በዚህ ድንጋጌ ሥር ከተጠቀሱት ታክሶች መካከል አንዱ ‹‹ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ የሚከፈል ታክስ›› (withholding tax) ሲሆን፣ በዚህ የታክስ ዓይነት ላይ

የሶስተኛ ወገን የቀደምትነት መብት ተፈጻሚነት እንደማይኖራዉ ያሳያል፡፡ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 142/2008 አንቀጽ (1) (2) ድንጋጌ ተመሳሳይ ይዘት ያለዉ መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡ የፌዴራሉም ሆነ የተጠቃሹ ክልል የታክስ አስተዳደር አዋጆች አንቀጽ 39 (7) መሰረት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ባንኮች ዋስትና የተቀበሉባቸዉ ሀብቶች የቀደምትነት መብት የሚኖራቸዉ ብድሩ ከመሰጠቱ በፊት ታክስ ከፋዩ የታክስ እዳ የሌለበት መሆኑ በባለስልጣኑ የተረጋገጠ ሲሆን ብቻ መሆኑን ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንጻር ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ.184757 ላይ የሰጠዉ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ዉሳኔ ማየት ይቻላል፡፡

ከፍ ሲል ከተጠቀሰዉ የአዋጁ ድንጋጌ መረዳት እንደሚቻለዉ ባንኮች ዋስትና የተቀበሉባቸዉ ሀብቶች የቀደምትነት መብት ሊኖራቸዉ የሚችለዉ በድንጋጌዉ ሥር የተመለከቱትን ቅድመ ሁኔታዎች ሲሟሉ መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህም ባንኮች በሀብቶቹ ላይ ዋስትና ከመቀበላቸዉ በፊት ከታክስ ከፋዩ የሚፈለግ የታክስ እዳ መኖር አለመኖሩን ከግብር ሰብሳቢዉ ባለስልጣን ጠይቀዉ ባለስልጣኑም የታክስ ዕዳ የሌለበት መሆኑን በሰነድ የተደገፋ ማረጋገጫ የሰጠ እንደሆነ ብቻ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ባለስልጣኑ ይህን ማረጋገጫ የሚሰጠዉ በወቅቱ ታክስ ከፋዩ መክፈል ያለበት ግን ያልከፈለ የበሰለ የታክስ እዳ መኖር አለመኖሩን በሕጉ አግባብ በማጣራት መሆኑ ይታመናል፡፡ ባንኮች በሀብቶቹ ዋስትና ለመቀበል በፈለጉበት ወቅት ከታክስ ከፋዩ የሚፈለግ የበሰለ ታክስ ከሌላ ባለስልጣኑ የታክስ እዳ የሌለበትም በማለት የሰነድ ማረጋገጫ ይሰጣል ተብሎ ይገመታል፡፡

ከዚህ አንጻር አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የአሁን አመልካች ባለሀብትነታቸዉ የፈለማ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር የሆኑት እና ለክርክር መነሻ የሆኑት ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ የመያዣ ዉል በማድረግ ዋስትና በተቀበለባቸዉ ወቅት ከዚህ ማህበር የሚፈለግ የታክስ ክፍያ መኖር አለመኖሩን ከተጠሪ መ/ቤት በመጠየቅ ተጠሪም የሰነድ ማረጋገጫ ሰጥቶት ነበር ወይስ አልነበረም? እንዲሁም በወቅቱ ማህበሩ ‹‹ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ የሚከፈል ታክስ›› (withholding tax) ለመንግስት መከፈል የሚገባቸዉ የበሰለ የታክስ እዳ ነበረ ወይስ አልነበረም? የእነዚህ ሁለት ነጥቦች ተጣርቶ የቀረቡ እንደሆነ ከቀደምትነት መብት አንጻር ያለዉ ሕጋዊ ዉጤት ምንድን ነዉ? የሚሉት ነጥቦች አግባብነት ባለዉ ማስረጃ ተጣርቶ በሕጉ አግባብ ዉሳኔ ሊሰጥባቸዉ የሚገባቸዉ ጉዳዮች ሆኖ አግኝተናቸዋል፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች የግራ ቀኙን ክርክር በዚህ አግባብ አጣርቶ መወሰን ሲገባቸዉ ይህን ሳያደርጉ የሰጡት ዉሳኔ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.136፣ 264፣ 327 (3)፣ 345 እና 246-249 ድንጋጌዎች ይዘትና ዓላማ የሚቃረን በመሆኑ ተቀባይነት የለዉም

ብለናል፡፡ ከዚህ አንጻር ይህ ሰበር ችሎት በሰ.መ.ቁ. 37105፣ 166617፣ 186816 እና በሌሎች መዛግብት ላይ የሰጠው አስገዳጅ ዉሳኔዎችን ማየት ይችላል፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች ከፍ ሲል በተጠቀሰዉ አግባብ አመልካች ለክርክር መነሻ የሆኑትን ተሸከርካሪዎች በመያዣ ዉል ዋስትና ሳይቀበልባቸዉ በፊት ለተጠሪ መ/ቤት ከዚህ ማህበር የሚፈለግ የታክስ እዳ መኖር አለመኖሩን የሰነድ ማረጋገጫ ማስረጃ ተሰጥቶት ነበር ወይስ አልተሰጠዉም? አመልካች ለክርክር መነሻ በሆኑትን ተሸከርካሪዎች ላይ ዋስትና ሳይቀበልባቸዉ በፊት ከማህበሩ የሚፈለግና ለመንግስት ያልተከፈለ የበሰለ ‹‹ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ የሚከፈል ታክስ›› (withholding tax) ነበር ወይስ አልነበረም? እንዲሁም የእነዚህ ጉዳዮች ከቀደምትነት መብት አንጻር ያላቸዉን ሕጋዊ ዉጤት ሳያጣሩ ያሳለፉት ዉሳኔ ባልተጣራ ጉዳይ ዉሳኔ እንደመስጠት ስለሚቆጠር መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ዉሳኔ**</u>

1. የአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የመ.ቁ.15079 በ6/4/2015 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የመ.ቁ.12334 በ5/7/2015 ዓ.ም የሰጠዉ ወሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍርድ የዘጋዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ በፍርድ ሐተታዉ በተመለከተዉ አግባብ ጉዳዩን በማጣራት ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ እንዲሰጥበት በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9 (2) መሰረት ተመልሶለታል፡፡
3. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
4. ግራ ቀኛቸዉ የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ የራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ም

**ማስታወሻ፡** - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

**የሰበር መ/ቁ 245687**

**ጥቅምት 06ቀን 2017ዓ/ም**

**ዳኞች:-** ሽመክት አሰፋ

ገበየሁ ፈለቀ

ዓለማየሁ ሹናራ

ተናኘ ጥላሁን

ዘዉዲቱ ታደሰ

አመልካች፡-ቢውቲፋል ቢንስ አግሮ ኃ/የተ/የግል ማኀበር-አልቀረቡም ከተባለ በኂላ ጠ/ፋሲል ቀረቡ

ተጠሪ ፡- ሰሙኤል ሪል አስቴት ኃ/የተ/የግል ማኀበር-ጠበቃ አምሳሉ ባዩ -ቀረቡ

መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የቤት ኪራይ ውልን የሚመለከት ሲሆን በስር ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 252600 በነበረዉ ክርክር አመልካች በይግባኝ እና በአሁን በሰበር ክርክሩ ውስጥ ካልተካተቱት ወ/ሮ ቤተልሄም ጥላሁን ጋር እንደ ቅደም ተከተላቸው 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች በመሆን የተከራከሩ ሲሆን የአሁን ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ተጠሪ ሐምሌ 15 ቀን 2012 ዓ.ም በአመልካች እና ስራ አስኪያጅ በሆኑለት ወ/ሮ ቤተልሄም ጥላሁን ላይ ባቀረበው ክስ ከአመልካች ጋር በተፈፀመ ኪራይ ውል ስምምነት መነሻነት ስራ አስኪያጇ ለተጠሪ ሊከፍሉት የሚገባው የኪራይ ገንዘብ ብር 2,266,318 ያለባቸው ስለመሆኑ በባንክ ቼክ ቢያረጋግጡም ክፍያውን ሊከፍሉ ያልቻሉ ከመሆኑም በላይ ቁልፍ

ሳያስረክቡ ቤቱን ለሌላ ሰው ማከራየት ትችላለህ በማለት በቀን 17/07/2012 ዓ.ም ደብዳቤ በመፃፍ ውል ካቋረጡ በኋላ እቃ አውጥቶ ቤቱ በ21/09/2012 ዓ.ም አስረክቧል፡፡ ይሁን እንጂ ቼኩ ስንቅ የሌለዉ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም ተከሳሾች ባልተነጣጠለ ኃላፊነት በቼኩ ላይ የተገለፀው የገንዘብ መጠን ብር 2,266,318.12 ገንዘቡ መክፈል ከነበረበት ከየካቲት 24 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍሉ፣ ዕቃ አዉጥተዉ ቤቱን እስካስረከቡበት ከ13/06/2012 ዓ.ም እስከ 21/09/2012 ዓ.ም ድረስ ያለው ውዝፍ የቤት ኪራይ 1,515,616.05፣ ለመጸዳጃ ቤት ግንባታ ወጪ ብር 439,558.86፣ ለጄኔሬተር ነዳጅ ወጪ ብር 51,173.93 በድምሩ ብር 4,272,695.96( አራት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሰባ ሁለት ሺ ስድስት መቶ ዘጠና አምስት ብር ከዘጠና ስድስት ሳንቲም) ክሱ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ እና ወጪና ኪሳራ ጋር ተከሳሾች ባልተነጣጠለት ኃላፊነት እንዲከፍሉት እንዲወሰንለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

የአሁን አመልካች ከ2ኛ ተከሳሽ ጋር በመሆን በቀን 18/05/2012 ዓ.ም በተፃፈ በሰጡት መልስ የቼክ ክፍያው የተፈፀመለት መሆኑን ፣ተጠሪ ያከናወነው ስራ የመፀዳጃ ቤት ከቤት ኪራዩ ጋር የሚካተት በመሆኑን እና የጄነሬተር የነዳጅ ክፍያ ጥያቄው በማስረጃ ያልተረጋገጠ ስለሆነ ሊጠየቁ የማይገባ መሆኑን፤ በቀን 17/07/2012 ዓ.ም የውል ማቋረጥ ደብዳቤ ፅፈው እቃ ሊያወጡ ሲሉ የከለከላቸዉ ተጠሪ መሆኑን፣ ማስጠንቀቂያ የጻፈላቸዉ ቢሆንም በውል ስምምነቱ መሰረት ጉዳዩን አስቀድሞ በድርድር ለመፍታት ጥረት ሲያደረጉ የቆዩ መሆኑን፤ በመቀጠል ለአሁን ተጠሪ የቼክ ክፍያው ቢፈፀምለትም የያዘውን ንብረት አለቅም በማለቱ ፖሊስ ወንጀል ክስ አቤቱታ ያቀረቡ መሆኑን፤አመልካች የራሱ የህግ ሰውነት ያለው ድርጅት በመሆኑ 2ኛ ተከሳሽ የድርጅት ስራ አስኪያጅ በመሆናቸው ብቻ መከሰሳቸው ተገቢ አለመሆኑን በመዘርዘር ክሱ ዉድቅ እንዲደረግላቸዉ ጠይቀዋል፡፡

ክርክሩ በዚህ መልክ የቀረበለት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክሱን ሰምቶ በማስረጃ የሚጣሩ ጉዳዮችን ካጣራ በኃላ በግራ ቀኙ በኩል የቀረቡትን ክርክሮች እና ማስረጃዎች መርምሮ በቼኩ ላይ የተመለከተዉን ገንዘብ ክርክሩ ከቀረበ በኃላ የተከፈለ ሲሆን ወለዱን በተመለከተ አመልካችና 2ኛ ተከሳሽ በአንድነት እና በነጠላ ባልተነጣጠለ ኃላፊነት እንዲከፍሉ፤ተጠሪ የአመልካችን ዕቃዎች ለማዉጣት ቁልፍ ጠይቆ አመልካች ቁልፍ የከለከለዉ መሆኑን ያላስረዳ መሆኑን በመጨረሻም ግንቦት 21 ቀን 2012 ዓ/ም የአመልካችን ዕቃዎች ተጠሪ አዉጥቶ በራሱ መጋዘን ማስቀመጡ አስቀድሞ ሊያከናዉነዉ ይገባ የነበረ ተግባር መሆኑን የሚያሳይና ኪሳራ የመቀነስ ኃላፊነቱን ያልተወጣ መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ አመልካች ውዝፍ ኪራይ የመክፈል ኃላፊነት የለበትም፣

የጀነሬተር ነዳጅ ክፍያው በተመለከተም በማስረጃ ያልተረጋገጠ በመሆኑ እንዲሁም የመጸዳጃ ቤት ለመገንባት የወጣዉን ወጪ በተመለከተ ይህንን ወጪ ለመተካት የገባዉ የዉል ግዴታ ስለሌለ አመልካች የመክፈል ሃላፊነት የለበትም ሲል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር የተሰኙት የአሁን ተጠሪ ቅሬታቸዉን በይግባኝ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ጠቅላይ ፍርድ ቤቱም ተጠሪ ከ13/06/2012 ዓ/ም ጀምሮ እስክ 21/09/2012 ዓ/ም ድረስ ያለዉን ዉዝፍ የቤት ኪራይ እንዲከፈለዉ የጠየቀ ሲሆን አመልካች በስር ፍርድ ቤት ሆነ በዚህ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክርክር ለውዝፍ ኪራዩ ኃላፊነት የለብኝም የሚል ይዘት ያለው ከመሆኑ ውጪ ዕቃዎቹን ያወጣዉ በቀን 21/09/2012 ዓ.ም አለመሆኑን በመካድ ያቀረቡት ክርክር የለም፤ የአሁን አመልካች ዕቃዎቹን ተከራይቶት በነበረዉ ቤት ዉስጥ ቆልፎ እስከ 21/09/2012 ዓ/ም ድረስ መቆየቱ እና በመጨረሻም ቤቱ ተከፍቶ ዕቃዉ የወጣዉ በአመልካች በቀረበዉ ቁልፍ ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት በቀረቡት ማስረጃዎች በተረጋገጡበት ሁኔታ ኪራይ ሊከፈል አይገባም ሊባል የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ የስር ፍርድ ቤት አመልካች የተጠየቀዉን ኪራይ ሊከፈል አይገባም የሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰዉ ተጠሪ የአመልካችን ዕቃዎች ለማዉጣት ጠይቆ አመልካች ቁልፍ የከለከለዉ መሆኑን አላረጋገጠም፤በመጨረሻም ግንቦት 21 ቀን 2012 ዓ/ም የአመልካችን ዕቃዎች በራሱ መጋዘን ማስቀመጡ አስቀድሞ ሊያከናዉነዉ ይገባ የነበረ ተግባር መሆኑን የሚያሳይና ኪሳራ የመቀነስ ኃላፊነቱን ያልተወጣ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነዉ የሚል ምክንያት በመስጠት መሆኑን የተጠቀሱት ምክንያቶች አመልካች እንደ ተከራይነቱ ቤቱን ሲለቅ የተከራየዉን ቤት ነጻ አድርጎ ለአከራዩ የማስረከብ በዉልና በህግ የተቀመጠዉን ግዴታዉን ከግምት ዉስጥ ያላስገቡ በመሆናቸዉ አመልካችን ሙሉ በሙሉ ከኃላፊነት ሊያድኑ የሚችሉ ባለመሆናቸውና በማስረጃም የተደገፉ በመሆናቸዉ የአሁን ተጠሪም በከፊልም ቢሆን ኪሳራ የመቀስ ግዴታዉን ያልተወጣ በመሆኑ በፍ/ህ/ቁ 1802 መሰረት ኪሳራዉን ግራ ቀኙ በእኩል ድርሻ ሊጋሩት የሚገባ በመሆኑ ተጠሪ ከጠየቀዉ የኪራይ ክፍያ ዉስጥ ግማሹን ብር 757,807.50 (ሰባት መቶ ሀምሳ ሰባት ሺ ስምንት መቶ ሰባት ብር ከሃምሳ ሳንቲም) አመልካች ሊከፍል ይገባል ፤ ለጄኔሬተር ነዳጅ አገልግሎት የወጣ እና ለመጸዳጃ ቤት ግንባታ የወጣ ወጪ አመልካች ሊከፍል አይገባም መባሉ ግን ተገቢነት ያለዉ ነዉ ሲል የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ የስጠውን ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት አሻሽሎ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ላይ ሲሆን የቅሬታዉ አጭር ይዘትም፡- አመልካች በተጠሪ ህንጻ ላይ ተከራይቶ ከሃምሌ 2010 ዓ/ም የውል ግንኙነቱ እስከተቋረጠበት እስከ መጋቢት 17 ቀን

2012 ዓ/ም ድረስ ሲሰራ መቆየቱን ዉሉ ከመቋጡ ማለትም ከመጋቢት 17 ቀን 2012 ዓ/ም በፊት በነበሩት ሁለት ሶስት ቀናት ከድርጅቱ ባለቤት ጋር በነበረው ውይይት ውሉን ለማቋረጥ የቃል ስምምነት ስለነበረ በካፌው ውስጥ የነበሩትን እቃዎቻችንን ለማውጣት ጥረት ስናደርግ ከአንድም ሁለት ሶስት ግዜ ዘበኞቹም ሆኑ ሌሎቹ ሰራተኞች ምንም አይነት ንብረት እንዳናወጣ የከለከሉን መሆኑን አረጋግጠናል ። ዉል ያቋረጥን መሆኑን መጋቢት 17 ቀን 2012 ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ አሳዉቀናል ። በውል ማቋረጫ ደብዳቤ ላይም ተጠሪ ቤቱን ማከራየት እንደሚችል የተጠቀሰ ሲሆን ነገር ግን እቃዎቻችንን እናዳናወጣ በሰራተኞቹ አስከልክሎን ሲያበቃ መጋቢት 21 ቀን 2012 ዓ/ም ለአመልካች በጻፈው ደብዳቤ እስከ ሚያዝያ 18 ቀን 2012 ዓ/ም ድረስ ያለባችሁን ውዝፍ ኪራይ ከፍላችሁ እቃውን ካላወጣችሁ እቃውን ራሴ አውጥቼ ወደ ራሴ መጋዘን በማስገባት ለሌላ ሰው ቤቱን አከራየዋለሁ በማለት ማስጠንቀቂያ ሲሰጠን ወዲያውኑ በ25/07/2012 ዓ/ም በጻፍነው ምላሽ የምንከፍለው ክፍያ እንደሌለን ነገር ግን እንዳለው እቃውን አውጥቶ በመጋዘኑ በማስቀመጥ በመያዣነት ሊጠቀምበት እንደሚችል በመግለጽ ምላሽ ሰጥተነዋል።እነዚህ የደብዳቤ ቅይይሮች በስር ፍ/ቤት መዝገብ ውስጥ ይገኛሉ።ተጠሪው እስከ ሚያዝያ 18 ቀን 2012 ዓ/ም ክፍያ ካልከፈላችሁ እቃውን አውጥቼ ወደ መጋዘን በማስገባት ቤቱን አከራየዋለሁ እንዳለው እና እኛም በ25/07/2012 ዓ/ም በሰጠነው ምላሽ እቃውን አውጥቶ ወደ መጋዘን ውስጥ ማስገባት እና ቤቱን ማከራየት ሲችል፣ተደጋጋሚ መሰል ደብዳቤዎችን እየጻፈ እና እስከዚህ ግዜ ድረስ ከፍላችሁ ካላጠናቀቃችሁ ምስክር ባለበት እቃውን አውጥቼ አከራየዋለሁ በማለት ብቻ ጊዜውን የፈጀ እና ቤቱን ለሌላ ሰው በማከራየት ጉዳቱን የማስቀረት ግዴታ እያለበት ቤቱ እንደተዘጋ እና እቃቹም እንደተቆለፈባቸው እስከ 21/09/2012 ዓ/ም ድረስ እንዲቆዩ ያደረገ በመሆኑ በ21/09/2012 ዓ/ም ደግሞ የናንተን ተወካይ ላኩልኝ ባለው መሰረት ተወካያችንን ልከን ንብረቶቹን ቆጥሮ ወደ ራሱ መጋዘን በማስገባት ቤቱን ንጹህ ያደረገ ሲሆን አመልካች አስቀድሞም እስከ ሚያዝያ 18 ቀን 2012 ዓ/ም ድረስ ከፍላችሁ ካልወሰዳችሁ ንብረቱን ወደ መጋዜኔ አስገባዋለሁ ሲል እስከ ሚያዝያ 18 ቀን 2012 ዓ/ም አትታገሰን ወደ መጋዘንህ አስገባው ለክፍያ ዋስትናም ይሆንሃል እያለ ፈቃደኝነቱን እየገለጸ ተጠሪው እቃውን እንዳለው ወደ መጋዘኑ ማስገባት እየቻለ ሆነ ብሎ ከቅን ልቦና ውጪ እስከ ግንቦት 21 ቀን 2012 ዓ/ም ገፍቶ ፣እንዲሁም አመልካች በ12/08/2012 ዓ/ም ለተጠሪው በጻፈው ደብዳቤ እቃቹን እንዲለቅለት የጠየቀ ቢሆንም ተጠሪው ምላሽ አለመስጠቱ በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ጉዳይ ነው።

በክሱ ሂደት ላይ እያለን ውዝፉን የ6 ወር ኪራይ ማለትም ከጥቅምት ወር 2012 ዓ/ም እስከ ለቀቅንበት መጋቢት ወር 2012 ዓ/ም ድረስ ያለብንን ክፍያ የፈጸምን ሲሆን ክርክሩ ከየካቲት 13 ቀን 2012 ዓ/ም ጀምሮ እስከ 21/09/12 ዓ/ም ድረስ ያለውን ውዝፍ ብር 1515616(አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ አስራ አምስት ሽህ ስድስት መቶ ስራ ስድስት ብር ) ክፈሉኝ የሚለው ላይ ቀጥሎ የስር ፍ/ቤቱ እቃዎቹን እንዳናወጣ ምክንያት የሆነው ራሱ ተጠሪ የነበረ መሆኑን እና ራሱ የእቃዎቹን ማውጫ ግዜ እያራዘመ እና ግዴታውን በፈቃዱ እየተሸከመ እና መብቱን በፈቃዱ እየተወ በደብዳቤ ተጠይቆም እቃቹን እንዳናወጣ በዘበኞች የከለከለን መሆኑን በማረጋገጥ የስር ፍ/ቤቱ ከ13/06/12 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ግንቦት 21 ቀን 2012 ዓ/ም ያለውን ኪራይ ክፈሉኝ ያለው አላግባብ መሆኑን አረጋግጦ ጥያቄውን ውድቅ በማድረግ ነገር ግን ያለብንን የምናምነውን እስከ መጋት 2012 ዓ/ም ያለብንን ውዝፍ ኪራይ የከፈልነው ነሃሴ 2012 ዓ/ም በመሆኑ ከመጋቢት እስከ ነሃሴ 2012 ዓ/ም ያለውነ ወለድ እንድንከፍል ያዘዘ ሲሆን ይህንንኑ ወለድ ከፍለን እቃዎቻችንን ከተረከብን በኋላ ተጠሪው ይግባኙን ለጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ አሁን ቅር የተሰኘንበትን ውሳኔ አስተላልፎብናል፡፡ የስር ፍርድ ቤቱ ከየካቲት 13 ቀን 2012 ዓ/ም ጀምሮ እስከ 21/09/12 ያለውን ውዝፍ ኪራይ ይከፈለኝ የሚለውን ጥያቄ በተመለከተ ሙሉ ለሙሉ ውድቅ ከማድረግ ውጪ ከየካቲት 13 ቀን 2012 ዓ/ም ጀምሮ ለሚለው የምን መነሻ እንደሆነ አልመረመረም ምክንያቱም አመልካች እስከ ለቀቀበት ማለትም መጋቢት ወር 2012 ዓ/ም ድረስ ያለውን የከፈለ በመሆኑ ነው፡፡ምናልበት ቤቱን ከለቀቅንበት ከመጋቢት 17 ቀን 2012 ዓ/ም ጀምሮ ያለውን ከሆነ በዚሁ ረገድ ሂሳቡም ተስተካክሎ ወራቱም ተቀንሰው መቅረብ የነበረበት ነዉ ይህ እንዲጣራ ባልተደረገበት ሁኔታ ከየካቲት 13 ቀን 2012 ዓ/ም የሚለው የምን መነሻ እንዳሆነ ሳይታወቅ፣ እንዲሁም ጠቅላይ ፍ/ቤቱ በውሳኔው ላይ አመልካች ውዝፍ ኪራይ የለብኝም ከማለት ውጪ እቃዎቹን ያወጣው በ21/09/12 አለመሆኑን በመካድ ያቀረበው ክርክር የለም፤ እቃቹ ላይ ቆልፎ እስከ 21/09/12 መቆየቱ እና በመጨረሻም በሩ የተከፈተዉ አመልካች ባቀረበው ቁልፍ ስለመሆኑ በስር ፍ/ቤት ተረጋግጧል ማለቱ ስህተት እና እቃዎቹ ላይ ቆልፌ የጠፋሁ የሚመስል አንድምታ ያለው ሲሆን ክቡር ጠ/ፍ/ቤቱ የጉዳዩን ሙሉ ስዕል አልወሰደም፡፡ ምክንያቱም በፍሬ ነገር ደረጃ እቃዎቹን ለማውጣት ተደጋጋሚ ሙከራ ሳደርግ መከልከሌን እና ተጠሪው እቃቹን እንዳወጣ እስከ ሚያዝያ 18 ቀን 2012 ዓ/ም ድረስ ወዶና ፈቅዶ ግዜ ሲሰጠኝ እኔ አመልካች አልፈልግም አውጣና በመጋዝን ውስጥ አስገባዋለሁ እንዳልከው አስገባው እያልኩ መሆኑን የሰነድ እና የሰው ማስረጃዎችን አቅርቤ አስረድቼ ባለበት እንዲሁም ባልተካደበት ሁኔታ የተከራየውን ቤት ነጻ አድርጎ ለአከራዩ ማስረከብ ነበረበት ማለቱ ስህተት ነዉ ፡፡ እቃቹን እኔም እንዳላወጣ ራሱም

ሳያወጣ ለቀረበት ግዜ ያውም ማራዘሚያ ግዜ እየሰጠኝ ባለበት ሁኔታ፣መጨረሻ ላይም በሩ የተከፈተው ተጠሪው ጋር ባለው ትርፍ ቁልፍ በሆነበት ሁኔታ ጠቅላይ ፍ/ቤቱ የተሳሳቱ መነሻዎችን በመያዝ እና ከክርክሩ አውድ እና ከቀረቡት ማስረጃዎች ውጪ የሆኑ ምክንያቶችን በመደርደር ከውዝፍ ኪራይ ውስጥ ግማሹን ብር 757807.50(ሰባት መቶ ሃምሳ ሰባት ሺ ስምንት መቶ ሰባት ብር ከ50/100) ከግንቦት 21 ቀን 2012 ዓ/ም ጀምሮ ተከፍሎ እስኪልቅ ድረስ ከሚታሰብ ወለድ ጋር እንድከፍል የሰጠዉ ዉሳኔ ስህተት ስለሆነ ሊሻር የሚገባዉ ነዉ የሚል ይዘት ያለዉ ነዉ

የሰበር ችሎቱም አመልካች ከተጠሪ ጋር ባደረጉት ስምምነት የኪራይ ውል ግንኙነቱን በማቋረጥ እቃቹን በማውጣት ሞክሮ በተጠሪ ሰራተኞች በተከለከለበት እና ተጠሪ እቃችን ወደ መጋዘን እንደሚያስገባ ባስታወቀው መሰረት አመልካች ፈቃደኝነቱን ገልጾ ባለበት ተጠሪ በራሱ አዘግይቶ ወደ መጋዘን እንዲገባ ባደረገበት ሁኔታ አመልካች ያልተጠቀመበትን ኪራይ ገንዘብ ግማሹን ለመክፈል በፍ/ብ/ህ/ቁ 1802 መሰረት ኃላፊ የመደረጉን አግባነትና ተያያዥ ነጥቦች በጭብጥነት በመያዝ ለመመርመር ያስቀርባል ብሎ ግራ ቀኙ ቀርበዉ ክርክር አድርገዉበታል፡፡

ተጠሪዉ ቀርቦ በሰጠዉ መልስ አመልካቹ ቤቱን የተከራየዉ ለካፌነት መሆኑን እስከ የካቲት 12 ቀን 2012 ዓ.ም. ድረስ ለነበረበት ውዝፍ የቤት ኪራይ በ24/06/2012 በተጻፈ የብር 2,266,318.12 የባንክ ቼክ ለተጠሪው ቢሰጥም በባንኩ በሚገኘው የአመልካቹ ሂሣብ ውስጥ ገንዘብ ስላልነበረ ቼኩ ሳይከፈል መቆየቱን ስለቼኩ አከፋፈል በሁለቱ ወገኖች ውይይት እየተደረገ እያለ አመልካቹ መጋቢት 17 ቀን 2012 ዓ.ም. በተጻፈ ደብዳቤ ውል አቋርጫለሁ በማለት መግለጹን ቀጥሎም በተከራየው ቤት ውስጥ የነበሩትን ዕቃዎች ለማውጣት ሙከራ ሲያደርግ፣ ተጠሪ ያለብህን ኪራይ ሳትከፍል ዕቃ ማውጣት አትችልም በማለት በፍትሐ-ብሔር ሕግ ቁጥር 2924 በተሰጠው መብት መሠረት የተከራዩን ዕቃዎች እንደያዘ ተጠሪው በ17/07/2012 ዓ.ም. በአመልካቹ የተጻፈውና ውል አቋርጫለሁ የሚለው ደብዳቤ ከደረሰው በኋላ፣ አመልካቹ የተከራየውን ቤት ቆልፎና ቁልፉን ይዞ በመሄዱ፣ ቤቱ ተከፍቶ፣ የሁለቱ ወገኖች (የተጠሪና የአመልካች /የአከራይና ተከራይ) ተወካዮች በተገኙበት ዕቃዎቹ ተፈታትተውና ተቆጥረው በመጋዘን እንዲቀመጡ፣ ቤቱ ለሌላ ሰው እንዲከራይ ተጠሪው(አከራዩ) አመልካቹን(ተከራዩን) በተደጋጋሚ በቃል፣በኢ-ሜል እና በጽሑፍ ቢጠይቅም አመልካቹ ፈቃደኛ እንዳልሆነና ቤቱን ቆልፎ እንደጠፋ በዚህም ምክንያት ቤቱ ለብዙ ወራት ያለሥራ (ሳይከራይ) ተዘግቶ መቀመጡን ተጠሪው በ14/09/2012 ዓ.ም. በተጻፈ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ፣በቼኩ ላይ የጻፈውን ገንዘብ፣ ከዚያ በኋላ ማለትም ከ13/06/2012 ዓ.ም.

ጀምሮ የተጠራቀመውን ውዝፍ ኪራይ እና የሚፈለግበትን ሌሎች ክፍያዎች ከፍሎ ዕቃዎቹን እንዲወስድ ለአመልካቹ መግለጹን ይህ ባይሆን በዕቃዎቹ ላይ ለሚደርሰው ጉዳት አላፊነት የማይወስድ መሆኑን ተጠሪው ገልጾ በዚህ ማስጠንቀቂያ መነሻት የአመልካቹ ተወካዮች ቁልፍ ይዘው መጥተው ቤቱ እንደተከፈተና የሁለቱ ወገኖች ተወካዮች በተገኙበት ዕቃዎቹ ተፈታትተው፣ ተቆጥረውና ተመዝግበው ሰነዱም በሁለቱ ወገኖች ተወካዮች ተፈርሞ ዕቃዎቹ በተጠሪው(አከራዩ) መጋዘን ውስጥ እንዲቀመጡ መደረጉን ተጠሪ ቤቱን በ21/09/2012 ዓ.ም መረከቡን ዕቃዎቹ በተጠሪው መጋዘን ውስጥ እንዲቀመጡ የተደረገው የኪራዩ ገንዘብ እስከሚከፈል ድረስ መያዣ እንዲሆኑ ነው፡፡ ይህም የሆነው በአመልካቹ ስምምነት መሆኑን ከዚህ በላይ እንደተገለጸው አመልካቹ የተጠሪውን ቤት የተከራየው ለአምስት(5) ዓመት የውሉ ዘመን 3 ዓመት ሲቀረው ምንም ዓይነት ማስጠንቀቂያ ሳይሰጥ በ17/07/12 ውሉን አቋርጫለሁ የሚል ደብዳቤ እንደጻፈ ያለብህን ውዝፍ ኪራይ ከፍለህ መልቀቅ ትችላለህ ሲባል ኪራዩን ለመክፈል ፈቃደኛ ያለመሆኑን፤ አመልካቹ የተከራየውን ቤት ከ13/06/12 እስከ 21/09/12 ቆልፎ መጥፋቱ፣ ቁልፉም በራሱ እጅ የነበረ መሆኑ በሥር ፍ/ቤት በተካሄደው ክርክር በራሱ (በአመልካቹ) የታመነ ከመሆኑም በላይ በማስረጃም የተረጋገጠ እንደሆነ አንድ ተከራይ የተከራየውን ቤት በራሱ ቁጥጥርና ይዞታ ሥር አድርጐ ለቆየበት ጊዜ ኪራይ መክፈል እንዳለበት የሚያከራክር ፍሬ-ነገር አይደለም፡፡ በመሆኑም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካቹ ቤቱን ይዞ ለቆየበት ጊዜ የኪራዩን ግማሽ ይክፈል ሲል የሰጠው ውሳኔ ተጠሪን የሚጐዳ እንጂ ከአመልካቹ አንጻር ፍትሀዊ መሆኑን ፤በ21/09/12 የቤቱ በር የተከፈተው በራሱ በአመልካቹ እጅ በነበረ ቁልፍ ነው፡፡ ይህም በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በተካሄድው ክርክር በማስረጃ የተረጋገጠ ነው፡፡ በአመልካቹ በራሱም የታመነ ፍሬ-ነገር ነበር፡፡ በመሆኑም አመልካቹ ያቀረበው ክርክር ተገቢ ባለመሆኑ ዉድቅ ተደርጎ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ሊጸና የሚገባዉ ነዉ የሚል ይዘት ያለዉ ነዉ፡፡

የሰበር አመልካችም የሰበር ቅሬታዉን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርቦ ክርክሩ ተጠቃሏል፡፡

አጠቃላይ የክርክሩ አመጣጥ እና ይዘቱ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን እኛም ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ በስር ፍርድ ቤቶች ከተደረገዉ ክርክር የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እና ለጉዳዩ ተገቢነት ካለዉ ህግ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል ፡፡ እንደመረመርነዉም ጉዳዩ ያስቀርባል ሲባል የተያዘዉ ጭብጥ አመልካች ከተጠሪ ጋር ባደረጉት ስምምነት የኪራይ ውል ግንኙነቱን በማቋረጥ እቃቹን በማውጣት ሞክሮ በተጠሪ ሰራተኞች በተከለከለበት እና ተጠሪ እቃዎችን ወደ መጋዘን እንደሚያስገባ ባስታወቀበት ሁኔታ እና አመልካች ፈቃደኝነቱን ገልጾ ባለበት ሁኔታ ተጠሪ በራሱ አዘግይቶ ወደ መጋዘን እንዲገባ በማድረጉ አመልካች ያልተጠቀመበትን

ኪራይ ገንዘብ ግማሹን ለመክፈል በፍ/ብ/ህ/ቁ 1802 መሰረት ኃላፊ የመደረጉን አግባነትና ተያያዥ ነጥቦች ለመመርመር ሲሆን እኛም በዚሁ ጭብጥ መሰረት መዝገቡን መርምረናል። እንደመረመርነዉም አንድ ግዴታ እንዲፈጸምለት የሚጠይቅ ሰዉ ሰዉ ለግዴታዉ መኖር ማስረጃ የማቅረብ እና የማስረዳት ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ህ/ቁ 2001 እንዲሁም በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 258 እስከ 261 ከተለከቱት ድንጋጌዎች መረዳት የሚቻል ነዉ። በፍታብሄር ጉዳይ እያንዳንዱ ተከራካሪ ወገን በክርክሩ ረቺ ሊሆን የሚችለዉ ተገቢዉን ማስረጀ አቅርቦ በእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት ክርክሩን ከሌላኛዉ ተከራካሪ ወገን በተሻለ ሁኔታ አስረድቶ በተገኘ ግዜ ነዉ።

በያዝነዉ ጉዳይ በስር ፌዴራል ከፍተኛዉ ፍርድ ቤት የተረጋገጠዉ እና በተጠሪም ያልተካደዉ ፍሬ ነገር የሰበር አመልካች ዕቃዎቹን ከተከራየዉ ካፌ ዉስጥ የካቲት 12 ቀን 2012 ዓ/ም በራሱ ለማዉጣት ሞክሮ በሰበር ተጠሪ ሰራተኞች የተከለከለ መሆኑ፤ ከዚያም መጋቢት 17 ቀን 2012 ዓ/ም የኪራይ ዉሉን ያቋረጠ መሆኑ፤ ዕቃዎቹን ተጠሪ ይዞ የቆየዉ የኪራይ ገንዘብ አልተከፈለኝም በሚል ለመያዣነት መሆኑ፤የሰበር ተጠሪዉ በወቅቱ ዕቃዎቹን ከካፌዉ አዉጥቶ እና መጋዘን ዉስጥ አስቀምጦ ቤቱን ለማከራየት እንዲችል የሰበር አመልካች ፈቃዱን ሲሰጥ የነበረ መሆኑ ነዉ።ተጠሪዉም ይህንኑ አደርጋለሁ እያለ ነገር ግን ሳይፈጽመዉ የቆየ መሆኑ ነዉ። ከዚህ መረዳት እንደሚቻለሁ አመልካች ዕቃዎቹን ያላወጣዉ መጀመሪያ በተጠሪዉ ሰራተኞች ተከልክሎ መሆኑን እና ተጠሪዉም ራሱ ዕቀዎቹን አዉጥቶ መጋዘን ዉስጥ አስቀምጦ ቤቱን ተከራይቶ መጠቀም እንዲችል ስምምነቱን ሲገልጽ የነበረ መሆኑን እና በቸልተኝነትም ይሁን ሆን ብሎ ተጠሪዉ ቤቱን አከራይቶ እንዳይጠቀም ያላደረገ መሆኑን ነዉ። የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ከዚህ የተለየ ማስረጃ አስቀርቦ በተጨማሪነት ባልሰማበት ሁኔታ የሰበር አመልካች እቃዎቹን ተከራይቶ በነበረዉ ቤት ዉስጥ ቆልፎ መቆየቱ ተረጋግጧል። የተከራየዉን ቤት ሲለቅ ዕቃዉን አዉጥቶ ነጻ አድርጎ የማስረከብ ግዴታዉን አልተወጣም በሚልና ጉዳት እንዲቀንስ አላደረገም በሚል በፍ/ብ/ህ/ቁ 1802 መሰረት ግማሽ ዉዝፍ ኪራይ ሊከፍል ይገባል ሲል መወሰኑ የተረገጠዉን ፍሬ ነገር እና የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 258፤261፤ የፍ/ብ/ህ/ቁ 2001 እንዲሁም የፍ/ብ/ህ/ቁ 1802፤ድንጋጌን መሰረት ያላደረገ ስለሆነ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ተብሎ ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል።

ዉሳኔ

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 226669 መጋቢት 29 ቀን 2015 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት የሰበር አመልካች አከራካሪዉ ቤት ተዘግቶ ለቆየበት ግዜ ዉዝፍ የኪራይ

ገንዘብ ብር 757807.50 /ሰባት መቶ ሃምሳ ሰባት ሽህ ስመንት መቶ ሰባት ብር ከሃምሳ ሳንቲም /ለሰበር ተጠሪ ሊከፍል ይገባል ሲል የሰጠዉ ፍርድ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል።

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 252600 ሚያዚያ 06 ቀን 2014 ዓ/ም የሰጠዉ ፍርድ ተገቢ የነበረ ነዉ ተብሎ ጸንቷል።

የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ ።

መዝገቡ ተዘገረቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መ/ቁ. 245726

ጥቅምት 6 ቀን 2017 ዓ/ም

**ዳኞች** ፡-ሽመልስ አሰፋ

ገበየሁ ፈለቀ

አለማየሁ ሹናራ

ተናኜ ጥላሁን

ዘውዲቱ ታደሰ

አመልካቾች፡-1. አቶ ማርሴል ታርዲ
2. አቶ አልቤር ታርዲ
3. ወ/ሮ ኤልሳቤት ፈላስፋው
} የቀረበ የለም

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሪት ኒና ታርዲ
2. አቶ ሮበርት ታርዲ
3. አቶ ፊሊፐ ታርዲ
} ጠበቃ አቶ መከተ ተፈራ -ቀረቡ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ሲሆን ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች ሚያዚያ 12 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 178185 ጥር 18 ቀን 2015 ዓ.ም እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት በመ/ቁ 30270 መጋቢት 8 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጧቸው ብይኖች መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

ክሱ አመልካቾች የፌ/ፍ/ቤቶች ፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት ፍ/ቤቱ በመ/ቁ 175618 የተሰጠውን ውሳኔ እንደፍርዱ እንዲያስፈጽም በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት እያስፈጸመ ስላልሆነ እንደፍርዱ እንዲፈጽም ይታዘዝልኝ በማለት የቀረበ አቤቱታን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የካ ምድብ 2ኛ ውርስ ችሎት ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር አመልካቾች የፍ/ባለዕዳዎች ተጠሪዎች ደግሞ የፍ/ባለመብት በመሆን ተከራክረዋል፡፡

አመልካቾች በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት አቤቱታ ይዘት የፌ/ፍ/ቤቶች ፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት በመ/ቁ 175618 የተሰጠውን ውሳኔ እንደፍርዱ እንዲያስፈጽም ትዕዛዝ የተሰጠው ቢሆንም ዳይሬክቶሬቱ ግራቀኞችን የውርስ ሀብት የሆነውን ቤት/ይዞታ በስምምነት በአይነት እንድንካፈል ተገቢውን ጥረት ሳያደርግ ዝቅተኛ የጨረታ መነሻ ዋጋ በማውጣት የውርስ ንብረቱ በግልጽ ጨረታ እንዲሸጥ ማድረጉ ህግን ያልተከተለ በመሆኑ የይዞታው እኩል ተከፍሎ ግማሹ እንዲሰጠን ይህ ከታለፈም በጨረታው ላይ ተሳታፊ እንድንሆን ይፈቀድልን በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

ከ1-3 ያሉት የፍ/ባለመብቶች በሰጡት መልስ የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት ስልጣን ባለው የመንግስት ተቋም የቀረበለትን መረጃ በመውሰድ እንደ ፍርዱ ለማስፈጸም በተሰጠው ስልጣን መሰረት ስራውን በህጉ አግባብ በመስራት የሀራጅ ጨረታ ማውጣቱ ዳይሬክቶሬቱን እንደፍርዱ ለማስፈጸም ጥረት አላደረገም ለማለት የሚያስችል ባለመሆኑ የፍ/ባለዕዳዎች አቤቱታ ከቅን ልቦና ውጪ ጊዜ ለማራዘም ታስቦ የቀረበ በመሆኑ ለደረሰብን መጉላላት ተገቢው ኪሳራ ይከፈሉን በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት የፍ/ባዕዳዎች ያቀረቡትን አቤቱታ እና መልስ ከተመለከተ በኋላ የአፈጻጸም ዳይሬክቶሬቱ በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት በውርስ ሀብቱ ላይ የሀራጅ ሽያጭ ያወጣው ይዞታውን በአይነት ለማካፈል የሚቻል መሆን አለመሆኑን ከሚመለከተው አካል በማረጋገጥ ፣ የፍ/ባለዕዳዎች ከ4ኛ የፍርድ ባለ መብት ጋር በመሆን ድርሻቸውን ለመውሰድ በመስማማት የውርስ ሃብቱን ከቀሪ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

ባለመብቶች ጋር በአይነት ለመካፈል አማራጭ ሃሳብ ማቅረብ አለማቅረባቸውን፤ አቅርበው ከነበርም ሳይፈጸም የቀረበትን ምክንያት እንዲሁም የጨረታ መነሻ ዋጋው አስቀድሞ ግራ ቀኙ እንዲያውቁት እና ተቃውሞ ያለው ሀሳቡን እንዲያቀርብ መደረግ አለመደረጉን ካልተደረገም ምክንያቱን አጣርቶ ምላሹን እንዲሰጥ ለዳይሬክቶሬቱ ትዕዛዝ ከሰጠ በኋላ የየካ ክፍለ ከተማ የመሬት ልማት እና አስተዳደር ጽ/ቤት ይዞታውን ለስድስት በአይነት እኩል ማካፈል እንደማይቻል፣ ይህ የሆነበት ምክንያትም በመመሪያ የተቀመጠውን ዝቅተና የቦታ ስፋት 150 ካ/ሜትር የሚያሟላ ባለመሆኑ እንደሆነ፣ የቦታ መጠኑን አስመልክቶ መረጃው የተወሰደውም ግራ ቀኙ በተገኙበት ስለመሆኑ የይዞታ አስተዳደሩ በ2/08/2014 ዓ/ም በጻፈው ደብዳቤ ላይ በመግለጽ ምላሽ ስለመስጠቱ፣ የፍርድ ባለዕዳዎች ጠበቃ በአቤቱታቸው እንዳሉት ክፍፍሉን ከ4ና የፍርድ ባለመብት ጋር በመሆን ይዞታውን ከቀሪ ባለ መብቶች ጋር እኩል ለመካፈል አማራጭ ሃሳብ ስለማቅረባቸው እሚገልጽ ማሸረጃ ባያቀርቡም በቀን 1/13/2014 ዓ/ም ለዳይሬክቶሬቱ በጽሁፍ የጠየቁት የፍርድ ባለዕዳዎች ብቻ ድርሻቸውን በጋር ይዘው ለመጠቀም ማስማማታቸውን በመግለጽ ሽምምነታቸውን የገለፁ ቢሆንም ይህ ስምምነታቸው 4ኛ የፍርድ ባለመብትንም ያካተተ ነው ቢባል እንኳ፤ በአንድ በኩል ለአፈጻጸሙ ለአፈጻጸሙ መነሻ የሆነው ውሳኔ የተሰጠው እያንዳንዳቸው ባለመብቶች በአይነት መካፈል ከተቻለ በአይነት እንዲካፈሉ በመሆኑ ዳይሬትቶሬቱ ከዚህ ውጪ ክፍፍል እሚፈጸምበት ህጋዊ ስልጣን የሌለው እና የፍርድ ባለዕዳዎች በጠየቁት መሠረት ክፍፍሉ እንዲፈጸም የሚፈልጉ ከሆነ ለችሎቱ አቅርበው ማስወሰን እንዳለባቸው የተገለጸላቸው በመሆኑ እና በዚህ መንገድ አስቅድመው ለችሎቱ ስምምነት አቅርበው ያሰጡት ትዕዛዝ ባለመኖሩ፤ በሌላ በኩል ጥያቄው ሊስተናገድ ይገባል ቢባል እንኳ የይዞታ አስተዳደሩ በሰጠው መልስ በአይነት ለማካፈል ከስድስቱ ወራሾች የአንዱ ድርሻ ከ150 ካሬ ሜትር ማነስ እንደሌለበት የገለጸ በመሆኑ የፍርድ ባለመብቶቹ ድርሻቸውን በጋራ ለመጠቀም እስካልተስማሙ ድረስ ከጠቅላላ ይዞታ መጠን 753 ካ/ሜ ላይ ከ150 ካ/ሜትር ላይ ከ150 ካሬ ሜትር ያላነሰ ይዞታ ለሦስቱ ባለመብቶች ለእያንዳንዳቸው ማለትም 450 ካሬ ሜትር ተቀንሶ፣ ለቀሪ ወራሾች በድርሻቸው ልክ መስጠጥ እስካልተቻለ ድረስ የፍርድ ባለዕዳዎች ከ4ና የፍርድ ባለመብት ጋርም ቢሆን ድርሻቸውን በጋራ ለመጠቀም በተስማሙት መሠረት ይዞታውን በአይነት ለመካፈል የሚችሉበት እድል እንደማይኖር በመረጋገጡ የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬቱ በውሳኔው መሠረት የውርስ ሀብቱን በአይነት ለማካፈል ተገቢውን ጥረት አላደረገም ሊባል ስለማይችል ዳይሬክቶሬቱ የውርስ ሀብቱን በአይነት ለማካፈል ተገቢን ጥረት አላደረገም በሚል የሀራጅ ሽያጩ እንዲቆም የፍርድ ባለዕዳዎች

ያቀረቡትን ተቃውሞ ውድቅ በማድረግ፣ የፍርድ ባለዕዳዎች በውርስ ሀብቱ ላይ በሚከናወነው የሀራጅ ሽያጭ ላይ እንዲሳተፉ በመፍቀድ ብይን ሰጥቷል ፡፡

አመልካች ይህንን ብይን በመቃወም ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም ብይኑ ሳይለወጥ ቀርቷል፡፡

አመልካቾች ሚያዚያ 12 ከ ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት አቤቱታ ይህን ብይን በመቃወም የቀረበ ሲሆን ይዘቱም በመ/ቁ 17618 በ06/05/14 በ573 ካ.ሜ ይዞታ ላይ 1/6ኛ እንድንካፈል ውሳኔ ተሰጥቶ እያለ 119 ካ.ሜ በመቀነስ ከተገለጸው ይዞታ መጠን መቀነስ እንደሚቻልና እንደማይቻል ፍርዱን ለሰጠው ወይም አፈጻጸሙን ለያዘው ፍ/ቤት የውሳኔ ማስተካከያ እርማት ሳይጠይቅ ከክ/ከተማው የመጣውን ምላሽ እንደ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመውሰድ በ454 ካ.ሜ ላይ ብቻ ጨረታ ማውጣቱ ከዋናው ፍርድ የሚጣረስ መሆኑን ጠቅሰን እንዲታረም ጠይቀን ይህንን በማለፍ አስተዳደሩ በሰጠው መረጃ መነሻነት ለተጫራቾች ግልጽነት ሲባል ይዞታው ተቀንሶ ጨረታው ላይ መውጣቱ አግባብ ያለው የጨረታ ሂደት ነው ይዞታችሁ አልተቀነሰባችሁም የጨረታ ማስታወቂያው ህጋዊ ነው በማለት የተሰጠው ብይን መሰረታዊ ህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡

ለክፍፍል የቀረበው ይዞታ 573 ካ.ሜ በመሆኑ በውሳኔው ላይ በተገለጸው አግባብ በአይነት ለ1/6ኛ ይከፈል ቢባል እያንዳንዳችን ወራሾች 95.5 ካ.ሜ የሚደርሰንና ካርታ ተሰርቶ ሊሰጠን የሚችል፤ በአሁኑ ጊዜም በሊዝ 72 ካ.ሜ ህንጻ እየተሰራበት እያለ ክ/ከተማው ከ150 ካ.ሜ በታች ሊካፈል አይችልም በማለት በሰጠው ምላሽ የትኛው መመሪያ እና ህግ እንደሚከለክል ባልተረጋገጠበት እና አመልካቾችም በምለሹ ላይ አስተያየት ባለስጠንበት ቀጥታ ወደ ጨረታ የተገባበት አግባብ እንዲሁም ስድስታችን በአይነት እንድንካፈል የተወሰነልንን መብት ተጠቅመን ሶስታችን አመልካቾች ግማሹ 286.5 ካ.ሜ በአይነት እንድንካፈል አማራጭ አቅርበን ለሁለት ተካፈሉ አልተባልም ተብሎ የተሰጠው ብይን የክፍፍል ውሳኔ ትርጉም የሚጥስና የተሳሳተ የማስረጃ ምዘና የተፈጸመበት የህግ ስህተት ነው፡፡

በ06/05/2014 ዓ.ም ውሳኔ ቅደም ተከተል መሰረት በክፍፍሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስብን በስምምነት ገዢ አፈላልገን ሽጠን ብንከፋፈል እና ብንስማማ አንዳችን ለሌላችን የገበያ ዋጋውን ከፍለን እንድናስቀር ዳይሬክቶሬቱንና የአፈጻጸም ችሎቱን ጠይቀን ቤቱ በዓይነት ሊካፈል አይችልም በማለት የውሳኔ ቅደም ተከተል ስለመፈጸሙ ሳያረጋግጥ በቀጥታ ወደ ሀራጅ የሄደበት አግባብ

ስህተት ነው ተብሎ የጨረታው ሂደት ቆሞ በአቤቱታችን ላይ የገለጽናቸው ስህተቶች ታርመው እንደውሳኔው ቅደም ተከተል እንዲፈጸምልን የስር ፍ/ቤት የሰጠው እና በከፍተኛ ፍ/ቤቱ የጸደቀው ብይን መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሰረዝልን የሚል ነው፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬቱ በራሱ ስልጣን የቤቱ ይዞታ መጠን በተመለከተ በካርታ ከተገለጸው 573 እንዲቀነስ በማድረግ በሀራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ ላይ የጠቃቀሳቸው ነገሮች ለአፈጻጸም መነሻ የሆነውን ዋናውን ፍርድ እና ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ሥነ-ስርዓት ህጉ ድንጋጌዎችን መሰረት ያደረገና ያገናዘበ መሆን አለመሆኑን ሊመረመር የሚገባ ሆኖ በመገኘቱ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪ ሚያዚያ 25 ቀን 2015 ዓ.ም በተጻፈ በሰጠው መልስ ዳይሬክቶሬቱ ስራውን በአግባቡ እና በህጉ መሰረት የንብረቱን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እና ከሚመለከተው የመሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት የመጣውን ምላሽ መሰረት በማድረግ ሁሉንም ስርዓቶች ተከትሎ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ የሀራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ ወጥቶ ስራውን የሰራ በመሆኑ በውሳኔው ቅደም ተከተል መሰረት ተገቢው ጥረት አልተደረገም በሚል እንዲሁም የቤቱ ይዞታ መጠንን በተመለከተ በራሱ ስልጣን በካርታ ከተገለጸው 573 ካ.ሜ እንዲቀንስ በማድረግ የሀራጅ ሽያጭ አውጥቶብናል በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ተገቢነት እና የህግ መሰረት የሌለው ነው፡፡

በሟች እናታችን ስም ያለው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ላይ ተገልጸው ያሉት በሙሉ በጨረታ ማስታወቂያው ላይ ተገልጸው ይገኛሉ፤ የየካ ክ/ከተማ የይዞታ አስተዳደር ፍርድ ያረፈበት ቤት በዓይነት መካፈል እንደማይችል ገልጾ ምላሽ በመስጠቱ የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬቱ ግራቀኛችን በስምምነት የምንፈጽመው ነገር ካለ ለሐምሌ 15 ቀን 2014 ዓ.ም አስተያየት እንድንሰጥ ባዘዘው መሰረት ተጠሪዎች በሀራጅ ተሸጦ እንዲከፈል ተስማምተን አስተያየት የሰጠን ሲሆን አመልካቾች በሽማግሌ እንጨርሳለን በማለታቸው ተጨማሪ 1(አንድ) ወር ቢሰጣቸውም ሊስማሙ ባለመቻላቸው የጨረታ ማስታወቂያው ህጉን ተከትሎ የወጣ በመሆኑ የቀረበው አቤቱታ ውድቅ ተደርጎ የደረሰብንን ወጪና ኪሳራ አመልካቾች እንዲከፍሉን ይወሰንልን በማለት መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡

አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የግራቀኙ ክርክርና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ብይን በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው። ይህ ችሎትም ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፣ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ህጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል።

ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ የቻልነው ፍሬ ጉዳዩን በማስረጃ የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 178185 በጥር 18 ቀን 2015 ዓ/ም በዋለው ችሎት ለሰጠው የአፈጻጸ ብይን መነሻ የሆነው ውሳኔ በመ/ቁ. 175618 በጥር 6 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት የተሰጠውን የፍርድ ቤቱን ውሳኔ ሲሆን፣ ውሳኔው በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 የቤት ቁጥር 155 የካርታ ቁጥሩ የካ/181416/06 የሆነው ይዞታ የሚኝ የውርስ ሀብት በመሆኑ የአሁን አመልካቾች እና ተጠሪዎች ንብረቱን በስምምነት እንዲዳፈሉ፣ በስምምነት መካፈል ካልቻሉ አንደኛው ወገን ለሌላኛው የንብረቱን ዋጋ በመክፈል ንብረቱን እንዲያስቀር. ይህም የማይቻል ከሆነ ጋራ ቀኙ ንብረቱን በስምምነት በመሸጥ ከሽያጩ የተገኘውን ገንዘብ በየድርሻቸው ይካፈሉ የሚል ነው።

በብይኑ ላይ እንደተመለከተው የሥር  ፍርድ ቤቱ የክርክሩ ምክንያት የሆነውን በካሬ ሜትር የይዞታው መጠን 573 ካሬ ሜትር ይዞታ በአይነት ለመካፈል የአንዱ ወራሽ ድርሻ ከስታንዳርዱ 150 ካሬ ሜትር ማነስ የሌለበት ሲሆን፣ ስታንዳርዱ ከግምት ሳይገባ የእያንዳንዱ  ውራሽ ድርሻ 573 ለስድስት ወራሾች ሲካፈል የእያንዳንዳቸው ድርሻ 95.5 ሲሆን፣ ይህ መጠን ከስታንዳርዱ 150 ካሬ ሜትር በታች በመሆኑ ለወራሾች በአይነት ለማካፈል የሚቻል አለመሆኑም መገንዘብ ተችሏል። በሌላም በኩል የሁለቱ ፍርድ ባለዕዳዎች ድርሻ፣ በጋራ ለመጠቀም ስምምነት ካደረጉት ከሦስተኛ የፍርድ ባለመበት ጋር 95.5 ካሬ ሜትር x በ3= 286 ካሬ ሜትር ስለሚሆን ከስታንዳርዱ በላይ ስለሚሆን ከጠቅላላው ይዞታ መጠን 573 ካሬ ሜትር ላይ ይህ 286 ካሬ ሜትር ሲቀነስ ቀሪው 287 ከ1-3 ተራ የተመለከቱት የሥር የፍርድ ባለመብት የሆኑ  የአሁን ተጠሪዎች ይዞታውን በጋራ ለመጠቀም ያልተስማሙ በመሆናቸው ቀሪው  የእያንዳንዳቸው ድርሻ 95.5 ብቻ በመሆኑና የእያንዳንዳቸው ድርሻ በስታንዳርዱ መሠረት ተገቢ የሆነውን 150 ካሬ ሜትር የማይደርስ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት ይዞታው በአይነት ለመካፈል የሚችል አይደለም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ እንዲሁም ይዞታው በአይነት ለመካፈል የማይችል መሆኑ ከላይ በተመለከተው ምክንያት በመረጋገጡ፣ የውርስ ሀብቱ  በጨረታ እንዲሸጥ የጨረታ ማስታወቂያ የወጣውም በውሳኔው ላይ ከተመለከተው የይዞታ መጠን ተቀንሶ አለመሆኑን የሥር ፍርድ ቤቱ

ካረጋገጠ በኋላ የአሁን አመልካቾች በጋራ ሀብቱ ላይ በሚደረገው የሐራጅ ሽያጭ እንዲሳተፉ መብታቸውን በመጠበቅ የሰጠው ብይን የአፈጻጸም መሰረት የሆነውን ውሳኔ ቅደም ተከተሎች የጠበቀና በቀዳሚዎቹ አማራጮች ክፍፍሉን ለማድረግ አለመቻሉን ካረጋገጠ በኋላ የመጨረሻውን አማራጭ በመያዝና የፍርድ ባለዕዳዎቹ በሐራጁ ሽያጭ ውስጥ ለመሳተፍ እንዲችሉ መብታቸውን በመጠበቅ የውርስ ሀብት ክፍፍሉ ንብረቱን በሐራጅ በመሸጥ እንዲከናወን በማለት የሰጠው ብይን መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ነው ብለናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት በመ/ቁ 30270 መጋቢት 8 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ብይን መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ ብይኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 ፀንቷል ፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻቻሉ፡፡
3. መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ::

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ም

<u>ማስታወሻ</u>፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መ/ቁ 245834

ጥቅምት 07 ቀን 2017 ዓ/ም

ዳኞች - ተፈሪ ገብሩ (ደ/ር)

እንዳሻዉ አዳነ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሰናይት አድነዉ

ሀፊዝ አባጀማል

አመልካች ፡- አቶ ደሱ ሃብቴ አሊ

ተጠሪ ፡- 1. አቶ ፍቃዱ ወ/ማርያም

2. አቶ አብርዶ ኢጅራ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከለታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ በፍርድ ላይ የተመለከተ የስም ስህተት እንዲታረም የቀረበ አቤቱታን የሚመለከት ነዉ፡፡ ጉዳዩ የተጀመረዉ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች ከሳሽ ተጠሪዎች ተከሳሽ ነበሩ፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው የስር ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች ባቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ መሰረት ተጠሪዎች ብር 250000.00 (ሁለት መቶ ሃምሳ ሺህ) እንዲከፍሉ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ከዚህ በኃላ

**ማስ ታወሻ፡** - ይህ የ ሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነ ድ ለ ጥና ትና ምር ምር ሥራ ወይምለ ግን ዛ ቤ እ ን ጂ ለ ፍር ድ አ ፈ ጻ ጸ ምዓ ላ ማአ ያ ገ ለ ግል ም!

አመልካች ለስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት አቤቱታ ተሻሽሎ በቀረበው ክስ የከሳሽ ስም ደሱ ሀብቴ ሲሆን ፍርድ ቤቱ በቀን 20/05/2014 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ አለአግባብ ደሳለኝ ሀብቴ ተብሎ የተመዘገበ ስለሆነ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 208 መሰረት የስም ስህተቱ ይታረምልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ፍርድ ቤቱ የቀረበዉን አቤቱታ መርምሮ ሀምሌ 06 ቀን 2010 ዓ.ም በተፃፈው ክስ የከሳሽ ስም ደሱ ሀብቴ ሳይሆን ደሳለኝ ሀብቴ ስለመሆኑ ለማየት ይቻላል፡፡ ስለሆነም በተሻሻለው ክስ መሰረት የከሳሽ ስም ደሱ ሀብቴ ተብሎ እንዲስተካከል የተጠየቀው በክሱ ላይ ደሳለኝ ሀብቴ ተብሎ ተመዝግቦ እያለ በመሆኑ አቤቱታው ተቀባይነት የለውም በማለት በትዕዛዝ ውድቅ አድርጓል፡፡

አመልካች ይህን ትዕዛዝ በመቃወም ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ይግባኙን ያስቀርባል ብሎ ከመረመረ በኃላ የስም አፃፃፍ ስህተቱ የተፈፀመዉ አመልካች የራሳቸውን ስም እየቀያየረ በመፃፋቸው ነዉ፤ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 208 መሰረት ፍርድ ቤት ስህተት የሚያርመዉ ስህተቱ በፍርድ ቤቱ የተፈፀመ በሆነ ግዜ ሲሆን በሌላ አነጋገር የስር ፍርድ ቤት ጥር 20 ቀን 2014 ዓ/ም በሰጠዉ ፍርድ የአመልካችን ስም ደሳለኝ ሀብቴ በሚል መሰየሙ ይህ ስም አመልካች ራሳቸው ያቀረቡለት እንጂ ፍርድ ቤቱ በራሱ ስህተት የሰየመዉ ስም ባለመሆኑ እንዲህ አይነት ስህተት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 208 የሚታረም ባለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ያሳለፈው ትዕዛዝ ሊፀና ይገባል በማለት ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው፡፡ አመልካች ሚያዚያ 13/2015 ዓ.ም ባቀረቡት የሰበር ማመልከቻ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ትክክለኛ ስሜ ደሱ ሀብቴ መሆኑን ገልጬ በትክክለኛ ስሜ ክሱን አሻሽየ እንድቀርብ ተፈቅዶልኝ ከሀምሌ 06 ቀን 2010 ዓ/ም በኃላ ጥቅምት 06 ቀን 2011 ዓ/ም በተሻሻለዉ ክስ ላይ ትክክለኛ ስሜ መገለፁን መዝገቡ የሚያስረዳ ሆኖ ሳለ አቤቱታዉ ዉድቅ መደረጉ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል፡፡ ትክክለኛ ስሜ የተመዘገበበት የተሻሻለ ክስ መዝገቡ ዉስጥ ሳይገኝ የቀረዉ የስር ፍርድ ቤት ክሱን በትክክለኛ ስሜ አሻሽየ እንዳቀርብ ፈቅዶ አሻሽየ ካቀረብኩ በኃላ በተሸሻለዉ ክስ መሰረት ክርክሩ ሲካሄድ ከቆየ በኃላ ሀምሌ 08 ቀን 2013 ዓ/ም በሰጠዉ ትዕዛዝ ከመዝገቡ እንዲወጣ በማድረጉ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት የመዝገቡን ይዘት ሳይመረምር አቤቱታዉን ዉድቅ ማድረጉ ስህተት ነው፡፡ ዉሳኔ የተሰጠዉ ለአመልች መሆኑን የስር ፍርድ ቤት እያወቀ የስም ስህተት ይታረምልኝ አቤቱታ ዉድቅ ማድረጉ በዉጤት ደረጃ የሰጠዉን ዉሳኔ ተፈፃሚ እንዳይሆን የሚያደረግ በመሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠዉ

ትዕዛዝ እና ዉሳኔ ተሽሮ መብት ባገኘሁበት ዉሳኔ ላይ የተጠቀሰዉ ስም የአመልካች ትክክለኛ ስም በሆነዉ ደሱ ሀብቴ ተብሎ ይታረምልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ቅሬታው ተመርምሮ አመልካች ለአቤቱታዉ መሰረት ያደረገዉ ስህተት ሊታረም የሚችል አይደለም በሚል የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠዉ ትዕዛዝ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተቀባይነት የማግኘቱን አግባብነት ይህ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 236245 ከሰጠዉ ዉሳኔ እንዲሁም በቀረበዉ አቤቱታ መነሻነት አመልካች ደሱ ሀብቴ በሚል ትክክለኛ ስሙ ክሱን አሻሽሎ እንዲቀርብ የስር ፍርድ ቤት ጳጉሜ 04 ቀን 2010 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት በሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረት አመልካች ጥቅምት 06 ቀን 2011 ዓ/ም አሻሽሎ ያቀረበዉ የክስ አቤቱታ ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ የነበር ከመሆኑ አንፃር ግራቀኝ በተገኙበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ጉዳዩ ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀርቡ ታዟል፡፡

ለተጠሪዎች በተደረገው ጥሪ መሰረት መልስ ይዘዉ ባለመቅረባቸዉ መልስ የማቅረብ መብታቸዉ ታልፏል፡፡ መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረው በዚህ ሁኔታ ነው፡፡

እንደመረመርነው አመልካች በውሳኔው ላይ የተፈጠረው የስም ስህተት እንዲታረምላቸው የጠየቁ ሲሆን ስህተቱ ሊፈጠር የቻለው አመልካች እራሳቸው አስቀድመው ባቀረቡት ክስ ላይ ስማቸው ደሱ ሀብቴ መባል ሲገባው ደሳለኝ ሀብቴ በማለት በመጥቀሳቸው ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ራሳቸው ባቀረቡት ክስ ላይ ደሳለኝ ሀብቴ ተብሎ የተመዘገበ በመሆኑ ይታረምልኝ አቤቱታው ተቀባይነት የለውም በማለት ትዕዛዝ የሰጠ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም በፍርዱ ላይ የአመልካችን ስም ደሳለኝ ሀብቴ በሚል መሰየሙ ይህን ስም አመልካች ራሳቸው ያቀረቡት እንጂ ፍርድ ቤቱ በስህተት የሰየመዉ ባለመሆኑ እንዲህ አይነት ስህተት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 208 የሚታረም አይደለም ብሏል፡፡

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 208 አንድ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ የተፈፀመ ስህተት ስለሚታረምበት ሁኔታ የሚደነግግ ሲሆን ስህተተቶቹም ባለማስተዋል የተፈጠሩ የጽህፈት ወይም የቁጥር ግድፈቶች ስለመሆናቸው ተመልክቷል፡፡ መሰል በድንጋጌው መሰረት ሊታረም የሚችል ስህተት እስከሆነ ድረስ ስህተቱ ሊፈጠር የቻለው በተከራካሪ ወገኖች ይሁን በፍርድ ቤቱ ልዩነት ሳይደረግ ሊታረም የሚችል ስለመሆኑ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 236245 ከሰጠው ትርጉም መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች ይታረምልኝ የሚሉትን ስም አመልካች ራሳቸው ያቀረቡት እንጂ ፍርድ ቤቱ በስህተት የሰየመዉ ባለመሆኑ እንዲህ አይነት ስህተት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 208 የሚታረም አይደለም በማለት የደረሱበት

መደምደሚያ እና ያሳለፉት ውሳኔ የድንጋጌውን ትክክለኛ ይዘት እና በሰበር ችሎቱ የተሰጠውን ትርጉም መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም። ከዚህም ሌላ አመልካች ደሱ ሀብቴ በሚል ትክክለኛ ስማቸው ክሱን አሻሽለው እንዲቀርቡ የስር ፍርድ ቤት ጳጉሜ 04 ቀን 2010 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት ትዕዛዝ ከሰጠ እና በዚሁ መሰረት አመልካች ጥቅምት 06 ቀን 2011 ዓ/ም አሻሽለው ካቀረቡ ከመነሻው ያቀረቡት ክስ ደሳለኝ ሀብቴ በሚል ክስ አቅርበው ነበር በሚል የስም ይታረምልኝ አቤቱታቸው ውድቅ የሚደረግበት የህግ ምክንያት የለም። ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች ያሳለፉት ትዕዛዝና ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል ብለናል።

ይልቁንም የአመልካች ትክክለኛ ስማቸው አስቀድመው በክሱ የገለፁት ደሳለኝ ሀብቴ ነው ወይስ ደግሞ ተሻሻለ በተባለው ክስ የተመከተው ደሱ ሀብቴ የሚለው የፍሬ ነገር ማጣራት ተደርጎ በእርማት አቤቱታው ላይ ተገቢው ትዕዛዝ ሊሰጥበት ይገባል። በመሆኑም ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የስር ፍርድ ቤት ትክክለኛ ስማቸው ማን እንደሆነ በመዝገቡ ውስጥ ከሚገኙ ሰነዶች እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች ማስረጃዎች አስቀርቦ በማጣራት አመልካች ትክክለኛ ስማቸው ደሱ ሀብቴ መሆኑን ከተረዳ ውሳኔው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 208 መሰረት እንዲታረም ሊያደረግ የሚገባ በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል።

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መዝገብ ቁጥር 259045 ሚያዚያ 19 ቀን 2014 ዓ/ም የሰጠዉን ትዕዛዝ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 293534 ጥር 18 ቀን 2015 ዓ/ም ያሳለፈው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል።

2. የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች ይታረምልኝ የሚሉትን ስም አመልካች ራሳቸው ያቀረቡት እንጂ ፍርድ ቤቱ በስህተት የሰየመዉ ባለመሆኑ እንዲህ አይነት ስህተት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 208 የሚታረም አይደለም በማለት ያሳለፉት ውሳኔ የድንጋጌውን ትክክለኛ ይዘት እና በሰበር ችሎቱ የተሰጠውን ትርጉም መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል።

3. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ በፍርዱ በተገለፀው አግባብ አጣርቶ ተገቢውን እንዲወስን ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 343(1) መሰረት መልሰናል።

4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ አመልካች የራሳቸውን ይቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ም

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ.መ.ቁ. 245889

ጥቅምት 05ቀን 2017ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ብርሃኑ መንግስቱ

ማርታ ተካ

አመልካች፡- ኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 ቤቶች ልማት ፅ/ቤት

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. አቶ ሸፋ ጀማል

2ኛ. ወ/ሮ ራዲያ ጀማል

**መዝገቡን በክረምት ስራ ተመርምሮ ተከታዩን ፍርድ ተሰጥተዋል፡፡**

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የመንግስት ቤትን የሚመለከት ክስን መነሻ ያደረገ ክርክር ሲሆን በአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች ከሳሽ የአሁኖቹ ተጠሪዎች ደግሞ 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች እንዲሁም ሌሎች በዚህ ሰበር መዝገብ ያልተካተቱ ከ3ኛ እስከ 15ኛ ተከሳሾች ሆነው ሲከራከሩ እንደነበር መዝገቡ ያመለክታል፡፡ ይህ ጉዳይ ለዚህ ሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የአዲስአበባ ከተማ መጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ለክርክሩ መነሻ የሆነው የመንግስት ቤት ለቀው ሊያስረክቡ ይገባል ሲል በመ/ቁ 39757፤ በቀን 20/8/2014ዓ.ም የወሰነውን፤ ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ ይህንኑ ውሳኔ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

በማሻሻል የአሁኑ ተጠሪዎች ከአመልካች ጋር የነበራቸው ውል ሊቋረጥ አይገባም እንዲሁም ቤቱንም ሊለቁ አይገባም ሲል በመ/ቁ 36812፤ መስከረም 30 ቀን 2015ዓ.ም መወሰኑም ሆነ የአዲስአበባ ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎትም ይህንኑ በማጽናት በመ/ቁ 39358፤ ጥር 17 ቀን 2015ዓ.ም ትእዛዝ መስጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ታርሞ የአዲስአበባ ከተማ መጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲፀናልን በማለት የሰበር አቤቱታ በማቅረብ በማመልከቱ ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ የአሁኑ አመልካች ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች እና ሌሎች አሁን በዚህ መዝገብ ያልተካተቱት ተከራካሪዎች የመንግስት ቤት እንዲለቁ አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን በአቤቱታቸውም፡- አመልካች የቀድሞው ወረዳ 24 ቀበሌ 17 የአሁኑ በኮ/ቀ/ክ/ከተማ ወረዳ 08 ልዩ ቦታው ቀጠና አንድ በሚባል አካበቢ አዋሳኞቹ በክስ ውስጥ የተገለፀው የመንገግስት ቤት የሆነ የቤት/ቁ 020 በ1988 ዓ.ም አየር ካርታ የሚታይ ከጭቃ የተሰራ 2 ክፍል መኖሪያ ቤት አንድ መፀዳጀ ቤት እና አንድ ማዕድ ቤት ለ1ኛ እና ለ2ኛ ተጠሪዎች ያከራየ ሲሆን የአሁኖቹ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች መንግስት ባከራያቸው መኖሪያ ግቢ ውስጥ ያለው ባዶ ቦታ ላይ በህገ ወጥ መንገድ ምንም አይነት የግንባታ ፈቃድ ሳይሳጣቸው የጭቃ ቤቶችን ገንብተው ከ3ኛ እስከ 15ኛ ላሉት ስር ተከሳሾች ቤቶቹን በህገ ወጥ መልኩ በማስተላለፋቸውና በመንግስት መመሪያ ቤቶች አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 4/2009 አንቀፅ 44(4)(5) መሰረት የመንግስት ቤትና ይዞታ ለሌሎች ለ3ኛ ወገን ማስተላለፍ የተከለከለ ሆኖ ሳለ ይህንኑ ክልከላ የተላለፉና የኪራይ ውል ዘመናቸውም የተጠናቀቀ በመሆኑ ሁሉም ተከሳሾች አላግባብ የያዙትን ቤት ለቀው ለአመልካች እንዲያስረክቡ እንዲወሰን ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ በሰጡት መልስ የቤት ቁጥር 020 የሆነውን የመንግስት ቤት በህጋዊ መንገድ ከአመልካች ተከራይቼ የምኖር ሲሆን ከአመልከች በኪራይ የያዝኩትን ቤትም አድሼና አሳምሬ እየኖርኩበት የምገኝ እንጂ ለሶስተኛ ወገን አላስተላለፍኩም ከዚህ ውጭ ያለው ይዞታ ከ1979 ዓ.ም ጀምሮ በስሜ የተመዘገበውንና ለእርሻ አገልግሎት ሳለማ የቆየሁት አስተዳደሩ የሚያውቀው የግል ይዞታዬ ይዞታዬ እንጂ መንግስት ቤት አካል ባለመሆኑ ክሱ ውድቅ ይደረግልኝ በሚል የተከራከሩ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ በኩል በስሜ የተመዘገበ ይዞታም ሆነ የመንግስት ቤት በሌለበት እንዲሁም አመልካች እኔን አስመልክቶ ያቀረበው ማስረጃ በሌለበት ሁኔታ መብትና ጥቅም ሳይኖረው ያቀረበው ክስ በመሆኑ ውድቅ መሆን አለበት በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ከ3ኛ እስከ 14ኛ የነበሩት ስር ተከሳሾች ተጠሪዎቹ ከሚኖሩበት የመንግስት ቤት ውጭ ንብረትነታቸው የ1ኛ ተጠሪ የነበሩትን ቤቶች በተለያየ ጊዜ በተደረጉ የቤት ሽያጭ ውል ስምምነት አመካኝነት ቤቶችን በግዢ ያገኙት ቤት እንጂ የመንግስት ቤት ባለመሆኑ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በሚል በሰጡት

መልስ የተከራከሩ ሲሆን 15ኛ ስር ተከሳሽ የተጠሪዎች ልጅ መሆኑን ጠቅሶ 1ኛ ተጠሪ ለእርሻ አገልግሎት ሲጠቀምበት ከቆየው የራሱ ይዞታ ውስጥ በስጦታ ተሰጥቶኝ ከ15 አመት በላይ እየኖርበት የምገኝ በመሆኑ አመልካች በዚሁ ይዞታ ላይ ክስ የማቅረብ መብትና ጥቅም የሌለው በመሆኑ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ግራቀኙን በጉዳዩ ላይ ካከራከረ በኃላ ተከራካሪዎች ካቀረቡዋቸው ሰነድ ማስረጃዎች በተጨማሪ ከሚመለከተው የኮ/ቀ/ክ/ከ የመሬት አስተዳደር የሽግግር ጊዜ ፕሮጀክት ጽ/ቤትና ቤቶች ልማት ጽ/ቤት በጋራ በመሆን ተገቢውን ባለሞያ ወደቦታው በመላክ ክርክር ያስነሳው ይዞታ በአየር ካርታ ሲታይ ምን ያህል እንደሆነ፤ ከ3ኛ እስከ 15ኛ ስር ተከሳሾች የያዙት ይዞታ በአየር ካርታ ሲታይ በቤ/ቁጥር 020 ግቢ ውስጥ የሚገኝ መሆን አለመሆኑ፤ ከ3ኛ እስከ 15ኛ ያሉት ተከሳሾች የያዙት ይዞታ በአየር ካርታ(GIS) ላይ መታየት አለመታየቱ ማጣራት ካደረገ በኃላ አመልካች ያቀረበው ክስ በከተማ አስተዳደሩ ታይቶ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት በቀጥታ ለፍ/ቤት ሊቀርብ የማይችል ነው በሚል ክሱን ውድቅ በማድረግ በ22/6/2011ዓ.ም ብይን ሰጥቶ የነበረ ቢሆንም የአ/አ/ከ/ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይህንኑ ብይን በመሻር ጉዳዩ በፍርድ የሚያልቅነው በማለት የስር ፍ/ቤት ከ3ኛ እስከ 15ኛ ያሉት ስር ተከሳሾች የሚኖሩበት ቤቶቹ የተገነቡት በቀበሌ ቤት ግቢ ውስጥ ነው ወይስ ከቀበሌ ቤት ይዞታ ውጪ፤ 1ኛ ተጠሪ የከተማ ቦታ የእርሻ መሬት ያላቸው ስለመሆኑ፤ ቤቶቹ የተሰሩት በዚሁ የእርሻ መሬት ላይ ስለመሆኑ፤ ግንባታው መቼ ተገነባ፤ የሚሉትን ጉዳዮች አጣርቶ ይወስን በሚል በመ/ቁ 30204፤ በቀን 16/11/2011ዓ.ም መልሶለታል፡፡

የአ/አ/ከተማ መጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት አጣርቶ እንዲወስን ከተመለሰለት በኃላ የተያዙት ጭብጦች መሰረት በማድረግ ከኮ/ቀ/ክ/ከ ወረዳ 08 ስራ አስፈጻሚ ጽ/ቤት 1ኛ ተጠሪ በወረዳው ውስጥ የእርሻ መሬት ያላቸው መሆን አለመሆኑ፤ ነበራቸው ከተባለ ከ3ኛ እስከ 15ኛ ያሉት ስር ተከሳሾቹ ቤት በዚህ እርሻ መሬት ላይ የተሰሩ መሆን አለመሆናቸውና መቼ እንደተሰሩ ማጣራት ተደርጎ እንዲቀርበለት እንዲሁም እነዚህ ተከሳሾች በስማቸው የተደራጀ የቤት ማህደር ካለም እንዲቀርብ ትእዛዝ በመስጠት ማጣራት ካደረገ በኃላ፡- ከ3ኛ እስከ 14ኛ ያሉት ተከሳሾች ከ1ኛ ተጠሪ ቤቶቹን ከመግዛታቸው አስቀድመው 1ኛ ተተሪ በዚሁ ቤትና ይዞታ ላይ መብት ያላቸው ስለመሆኑ ተገቢውን ጥንቃቄና ማጣራት ባለማድረጋቸው የቅን ልቦና ገዢዎች ናቸው ሊባሉ ስለማይችሉ እንዲሁም 15ኛ ስር ተከሳሽም በአሁኖቹ ተጠሪዎች በስጦታ ያገኘሁት ነው በሚል ቢከራከሩም ስጦታ አድራጊዎቹ የቤቱ ባለቤት ስለመሆናቸው ማስረጃ ያላቀረቡ በመሆኑ ከ3ኛ እስከ 15ኛ ስር ተከሳሾች የያዙዋቸው ቤቶች የመንግስት ቤት በሆነው የቤት ቁጥር 020 ይዞታ ክልል ውስጥ የሚገኙ በመሆኑና ቤቶቹ የተሰሩበት ይዞታም የ1ኛ ተጠሪ የእርሻ መሬት ባለመሆኑ ከ3ኛ እስከ 15ኛ ያሉት ስር ተከሳሾች

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

የያዙት ቤት ባለቤቶች ናቸው ሊያስብል የሚችል የህግ መሰረት የለም፤ ነገር ግን የአሁኖቹ ተጠሪዎች ከመንግስት የተከራዩት የቤት ቁጥር 020 አካል የሆነውን ባዶ ቦታ ላይ ቤት ገንበተው ማስተላለፋቸው ኪራይ ውሉን ለማቋረጥ ምክንያት አይሆንም በማለት በመመሪያ ቁጥር 5/2011 አንቀጽ 30(2፣5፣6) መሰረት ከ3ኛ እስከ 15ኛ ያሉት ስር ተከሳሾች የያዙዋቸው ቤቶች የኪራይ ተመን ወጥቶላቸው በተከራይነት ቢቀጥሉ የሕጉን አላማና ግብ ስለሚያሳካ የመንግስት ቤትን በኪራይ ለመያዝ የሚያስፈልጉ ቅድመሁኔታዎችን መሟላታቸውን ተረጋግጦ የሚያሟሉ ከሆነ በያዙዋቸው ቤቶች ላይ ተከራይ እንዲሆኑ የማያሟሉ ከሆነ ቤቶቹን ይልቀቁ በማለት ታህሳስ 13 ቀን 2012ዓ.ም የወሰነ ቢሆንም አሁንም ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱ በድጋሚ በመ/ቁ 362540፤ በቀን 26/4/250014ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ የስር ፍርድ ቤት ባልተጠየቀው ዳኝነት ውሳኔ መስጠቱ ሊታረም ይገባል በማለት ከተጠየቀው ዳኝነት አንጻር ጭብጦችን በመለየት አከራክሮ እንዲወስን መመለሱን ተከትሎ የስር ፍርድ ቤት ተጣርቶ እንዲወሰን ከተመለሰለት ጭብጥ አንጻር በጉዳዩ ላይ አከራክሮ እንደአጠቃላይ የቀረበው ማስረጃ መርምሮ በመ/ቁ 39757 በሆነ ላይ በቀን 20/08/2014 ዓ.ም ሲወስን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በኪራይ የያዙት ቤት አካል በሆነው የመንግስት ይዞታ ላይ መመሪያ ቁጥር 4/20009 አንቀፅ 25(2) ላይ የተቀመጠውን ኃላፊነት በመተላለፍ ህገ ወጥ ግንባታ በማካሄዳቸው አመልካች ውሉን እንዲያቋረጥ ምክንያት ሆነዋል፡፡ በመሆኑም ተከሳሾች(ተጠሪዎችን ጨምሮ) በኮ/ቀ/ክ/ከ/ወረዳ 08 የሚገኘውንና ለክርክሩ መነሻ የሆነውን የቤት ቁጥር 020 ለቀው ለተጠሪ ያስረክቡ በማለት ወስኗል፡፡

የአሁኖቹ ተጠሪዎች እና አሁን በዚህ መዝገብ ያልተካተቱት ሌላ ተከራካሪ ጋር በመሆን በውሳኔው ቅር በመሰኛት ይግባኝ ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም በመ/ቁ 36812 በቀን 30/01/015 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በተከራዩት ቤት ላይ የፈፀሙት ህገ ወጥ ተግባር ስለመኖሩ የተረጋገጠ ነገር ካለመኖሩም ባለፈ ቤቱን ለ3ኛ ወገን ስለማስተላለፋቸው የቀረበ ማስረጃ በሌለበት አግባብ የስር ፍ/ቤት 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች መልስ ሰጪ ጋር የነበራቸውን ውል ተቋጦ ቤቱንም መልቀቅ አለባቸው በማለት የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ሆኖ አግኝቼዋለሁ በማለት ስር 15ኛ ተከሳሽ ሆነው የተጠሪዎች ልጅ የያዘው ቤት መልቀቅ አለበት ተብሎ በስር ፍ/ቤት የተወሰነውን በማጽናት ሲወስን፤የአሁኑ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ከአመልካች ጋር የነበራቸው ውል ሊቋረጥ አይገባም፤ በውል ከያዙት ቤትም ሊለቁ አይገባም በማለት የስር ፍ/ቤቱን ውሳኔ በዚህ አግባብ በማሻሻል ወስኗል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎትም በመ/ቁ 39358 በቀን 17/05/2015 ዓ.ም በሰጣው ትዕዛዝ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በቀን 17/08/2015 ዓ.ም ጽፌ ያቀረበው አቤቱታ ይዘቱ ሲታይ፡- ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ተጠሪዎች የራሳቸው ንብረት ባልሆነው የቤት ቁጥር 020 በሚገኝበት ግቢ ውስጥ ህገ ወጥ ግንባታ ገንብተው ቤቶችን ሰርተው ማስተላለፋቸውን አምኖ እያለ በመንግስት ቤቶች አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 5/2011 አንቀጽ 38 (4) መሰረት አመልካች ውል ማቋረጥ ይችላል በሚል መወሰን ሲገባው ለክርክር ምክንያት የሆነውን የቤት ቁጥር 020ን እና ግቢውን ነጣጥሎ ማየቱ ስህተት ነው፡፡ በጊቢው መገንባታቸው ከተረጋገጠ በመመሪያ 5/2011 አንቀፅ 38(1)(4) መሰረት ውሉ ተቋርጦ ቤቱን ሊለቁ ይገባል፤ ቤቶቹ የተገነቡት በቤት ቁጥር 020 ይዞታ ክልል ውስጥ መሆኑን እና በተጠሪዎች የእርሻ መሬት ላይ አለመሆኑን የስር ፍ/ቤት በማስረጃ አረጋግጦ እያለ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ተጠሪዎች በተከራዩት ቤት ላይ ህገ ወጥ ተግባር ስለመፈጸማቸው የቀረበ ማስረጃ ስለሌለ ውላቸው ሊቋረጥ እንደማይገባ እና ቤቱንም መልቀቅ እንደሌለባቸው የሰጠው ውሳኔ የማስረጃ ምዘና ስርዓትን ያልተከተለ ስለሆነ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ይታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም ተጠሪዎች ከአመልካች በተከራዩት የቤት ቁጥር 020 ይዞታ ግቢ ውስጥ በሚገኝ ቦታ ላይ ቤት ሠርተው ለ3ኛ ወገን ማስተላለፊቸው ተረጋግጦ 3ኛ ወገኖች ቤቶቹን እንዲለቁ በተወሰነበት ሁኔታ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተጠሪዎች ለ3ኛ ወገን ስለማስተላለፋቸው ማስረጃ አልቀረበም በሚል ከተጠሪዎች ጋር የተደረገው የኪራይ ውል ሊቋረጥ አይገባም በማለት የመወሰኑን አግባብነት ከመሰረታዊ የክርክር አመራርና ማስረጃ ምዘና መርህ እንዲሁም ከመንግስት ቤቶች አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 5/2011 አንቀፅ 38 እና ተዘማጅ ድንጋጌዎች አንፃር ለማጣራት ሲባል ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት አዟል፡፡

ተጠሪዎችም በጠበቃቸው በኩል በቀን 04/06/2016 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት መልሳቸው አመልካች 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ተከራይተው የነበረው ቤት ለሌላ 3ኛ ወገን አስተላልፈው ሰጡ የሚል ክርክር አላቀረቡም፡፡ ተሰሩ የተባሉት ቤቶችም 1ኛ እና 2ኛ መልስ ሰጪዎች የሚኖሩባቸው ቤቶች አይደሉም፡፡ ይህ ከሆነ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪ በውል የተከራዩትን የቀበሌ ቤት ይዘው መኖራቸው ሕገወጥ ተግባር ፈፅመዋል የሚያስብላቸው አይሆንም፡፡ በደፈናው በቀበሌው ቤት አጠገብ የተሰሩ ቤቶች አሰርቷል የሚል የተሳሳተ ማስረጃ የሌለውና ለረዥም ዘመን በይዞታው ላይ ቤት የሰሩትን ሰዎች ህገወጥ ለማስመሰል ያቀረበው ክስ እንጂ 1ኛ እና 2ኛ መልስ ሰጪዎች የፈፀሙት ተግባር ስላልሆነ የአመልካች ክስ ተገቢ አለመሆኑን ያሳያል፡፡ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ከ30 ዓመት በላይ ከመንግስት ተከራይተን በምንኖረው ቤት ውስጥ እየኖርን የምንገኝ ሲሆን ይህንን ቤት ለሌላ ሰው አላስተላለፍንም ከእኛም ውጪ የሚኖርበት ሰው የለም፡፡ አመልካች ቤቶቹ መቼ እንደተሰሩ የማይጠቅስ ከመሆኑም በላይ በሥር

ፍ/ቤት በተደረገ ክርክር በጂአይ ኤስ እና በሲአይኤስ የአየር ካርታ በ97 ዓ.ም ላይ እንደሚታይ የአመልካች ተቋም ራሱ አረጋግጦ መልስ ሰጥቷል፡፡ ስለሆነም ሕገወጥ ቤት የለም እንጂ ህገወጥ ቤት ቢኖር እንኳን አመልካች ህገወጥ ቤት ይፍረስ ብሎ ክስ የማቅረብ ሥልጣንም የለውም፡፡ ህግ ወጥ ግንባታ ያለ ከሆነ መጠየቅ ያለበት ደንብ ማስከበር ፅ/ቤት መሆን አለበት፡፡ እንዲሁም ህግ ወደ ኋላ ለተፈፀመ ተግባር ተመልሶ የማይሰራ በመሆኑ አመልካች የጠቀሷቸው መመሪያዎች ለዚህ ጉዳይ ተገቢነት የሌለው ነው፡፡ በመሆኑም የአመልካች አቤቱታ ውድቅ መሆን አለበት በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ በማቅረብ ክርክራቸው አጠናክሮ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጣር ባለመልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረን ተጠሪዎች የቤት ቁጥር 020 የሆነው ቤት ተከራይተው እያለ እና በተከራዩት ቤት ስር በሚጠቃለል ይዞታ ላይ 1ኛ ተጠሪ ቤት ሰርተው ለሶስተኛ ወገን ማስተላለፋቸው በማስረጃ ተረጋግጦ እያለ፣ የቤት ቁጥር 020 ለሶስተኛ ወገን ያላስተላለፉ ስለሆነ ሊለቁ አይገባም ተብሎ በተሰጠ ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል ወይስ አልተፈፀመም የሚል ጭብጥ በመያዝ መዝገቡን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም በስር ፍርድ ቤት አመልካች የጠየቁት ዳኝነት ተጠሪዎች የቤት ቁጥር 020 የሆነው ተከራይቶ እያለ በቤት ቁጥሩ ስር የሚጠቃለል ይዞታ ላይ ምንም አይነት የግንባታ ፈቃድ ሳይሳጣቸው በህገወጥ መንገድ ቤት ሰርተው ለ3ኛ ወገን ያስተላለፉ ስለሆነ እና የኪራይ ጊዜው ያበቃ ስለሆነ ቤቱን ይልቀቁ የሚል ሲሆን ተጠሪዎች ደግሞ ለ3ኛ ወገን የተላለፈዉ ቤት በቤት ቁጥር 020 ስር የማይካተት መሆኑን እና የቤት ቁጥር 020 የሆነው ለ3ኛ ወገን ያላስተላለፉ መሆኑን ገልፀው የተከራከሩ መሆኑን ከመዝገቡ መገንዘብ ተችሏል፡፡

የአንድን ፍሬነገር መኖር የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባላቸው የአዲስአበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ሆነ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በተመሳሳይ ሁኔታ በማስረጃ የተረጋገጠው ፍሬነገር ተጠሪዎች ከቀበሌ የተከራዩት የቤት ቁጥር 020 አካል በሆነው ይዞታ ላይ አከራዩን ሳያሳውቁና ያለ ግንባታ ፈቃድ ቤቶችን ሰርተው ለሶስተኛ ወገን ማስተላለፋቸውን ነው፡፡ የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቱ ተጠሪዎች ከቀበሌ የተከራዩት ቤት አካል በሆነው የመንግስት ይዞታ ላይ ህገወጥ ግንባታ በማካሄዳቸው በመመሪያ ቁጥር 4/2009 አንቀጽ 35(2) መሰረት የውል ማቋረጫ ምክንያት በመሆኑ ለክርክሩ መነሻ የሆነው የተከራዩትን ቤት ቁጥር 0200 ለቀው ሊያስረክቡ ይገባል በሚል የወሰነውን ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ የሻረበት ምክንያት ተጠሪዎች ከቀበሌ በተከራዩት የቤት ቁጥር 020 ላይ የፈፀሙት ህገወጥ ተግባር ስለመኖሩ የተረገገጠ ነገር ካለመኖሩም ባለፈ የተከራዩትን

ቤት ለ3ኛ ወገን ስለማስተላለፋቸው በማስረጃ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ውላቸው ሊቋረጥም ሆነ ቤቱን ሊያስረክቡ አይገባም በሚል ነው፡፡

እንደሚታወቀው በቀድሞ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ የመንግስት ቤቶች አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 4/2009 አንቀጽ 35 ሆነ ከዛ ቀጥሎ በሥራ ላይ በነበረው መመሪያ ቁጥር 5/2011 አንቀጽ 38 እንዲሁም አሁን በስራ ላይ  በዋለው መመሪያ ቁጥር 140/2015 አንቀጽ 35 (8)፤54(3) ድንጋጌ  ተከራይ የተከራየውን ቤት፣ ይዞታ፣ ግቢና ንብረት በጥንቃቄ የመያዝና የመንከባከብ ግዴ ታ እንዳለበት፤ ተከራይ ሕገወጥ ግንባታ ገንብቶ ከተገኘ አከራይ በተከራይ ወጪ እንደሚያፈርስ፤ ውልንም ሊያቋረጥ እንደሚችል የሚደነግጉ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች የምንረዳው ተከራይ አከራዩን ሳያስፈቅድ ከተከራየው ቤት ጋር ባለው ይዞታ ላይ ግንባታ መገንባት እንደማይችልና ገንብቶ ሲገኝ አከራዩ ውሉን ሊያቋርጥ የሚችል መሆኑን ነው፡፡ ውሉ የማቋረጥም ሆነ ያለማቋረጥ መብት የሚሰጠው ለአከራዩ መሆኑን ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤቶች ተጠሪዎች ከተከራዩት የቤት ቁጥር 020 አካል በሆነው የመንግስት ይዞታ ላይ አከራዩን ሳያስፈቅዱና ያለ ግንባታ ፈቃድ ቤቶችን በመገንባት ለሶስተኛ ወገን ማስተላለፋቸው እስከተረጋገጠ ድረስ ተጠሪዎች የተከራዩት ቤት ብቻ ሳይሆን ከነይዞታው ጭምር በጥንቃቄ መያዝና በመንግስት ይዞታ ላይ ግንባታ ለመገንባትም የአከራዩ ፈቃድ መጠየቅ ሲገባቸው ፈቃድ ሳይጠይቁ ህገወጥ ግንባታ በመገንባት ለሶስተኛ ወገን ማስተላለፋቸው እስከተረጋገጠ ድረስ ይህ የተጠሪዎች ተግባር በመመሪያው መሰረት አከራዩ ውሉን ሊያቋርጥ ከሚችልበት አንዱ ምክንያት ሆኖ እያለ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተጠሪዎች የተከራዩት ቤትና ይዞታው የተለያየ እንደሆነ አድርጎ በመውሰድ ተጠሪዎች በተከራዩት ቤት አካል በሆነው የመንግስት ይዞታ ላይ ህገ ወጥ ግንባታ ገንብተው ለሶስተኛ ወገን ማስተላለፋቸው ቢረገገጥም በተከራዩት ቤት ላይ ህገወጥ ግንባታ መገንባታቸውም ሆነ ለሶስተኛ ወገን ማስተላለፋቸው አልተረጋገጠም በማለት ውሉ ተቋርጦ የተከራዩት ቤት ሊያስረክቡ አይገባም ማለቱም ሆነ የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎትም ይህንኑ ማረም ሲገባው ሳያርም መቅረቱ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መፈፀማቸውን የሚያሳይ በመሆኑ መታረም ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ሲጠቃለል ተጠሪዎች ከመንግስት የተከራዩትን የቤት ቁጥር 020 አካል በሆነው የመንግስት ይዞታ ላይ ህገወጥ የቤት ግንባታ ገንብተው ለሶስተኛ ወገን ማስተላለፋቸው በተረጋገጠበት ሁኔታ የተጠሪዎች ውል ሊቋረጥም ሆነ የተከራዩት የቀበሌ ቤት ሊለቁ አይገባም በሚል የከተማው ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቱን ውሳኔ በማሻሻል መወሰኑም ሆነ በከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት ይህንኒ ውሳኔ በማጽናቱ በቀድሞዉ መመሪያ ቁጥር 4/2009 አንቀጽ 35(2)ም ሆነ ቀጥሎ ባለዉ የመንግሥት ቤቶች አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 5/2011 አንቀጽ 38(1)፤(4) እንዲሁም አሁን በስራ ላይ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ባለው መመሪያ ቁጥር 140/2015 አንቀጽ 35 (8)፤54(3) ስር የተደነገገዉን መሰረት ያላደረገ በመሆኑ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2/4 እና 10(1) ስር በተደነገገዉ መሰረት መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ስላገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 36812 በቀን 30/01/2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የአዲስ አበባ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 39358 በቀን 17/05/2015 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 39757 በቀን 20/08/2014 ዓ.ም የሠጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
3. ተጠሪዎች በኮ/ቀ/ክ/ከ/ወ 08 የሚገኘውን ከቀበሌ የተከራዩት የቤት ቁጥር 020 ለቀው ለአመልካች ሊያስረክቡ ይገባል በሚል ተወስኗል፡፡
4. የዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ወጪና ክሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ም

የሰ/መ/ቁ:245896

6/2/2017

ዳኞች ሺመክት አሰፋ

ገበየሁ ፈለቀ

አለማየሁ ሹናራ

ተናኜ ጥላሁን

ዘውዲቱ ታደሰ

አመልካች፦ ወ/ሮ ርዕዩት አለም ጉዲሳ አልቀረቡም

ተጠሪዎች፦1 አቶ መስፍን ሃ/ማርያም

2 አቶ ፍቃዱ ሃ/ማርያም

3 ወ/ሮ ሂሩት ሃ/ማርያም

4 ወ/ሮ የኔነሽ ሃ/ማርያም

} አልቀረቡም ከተባለ በኃላ ጠበቃ አቶ ሽመልስ አድማሴ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በአዳማ ከተማ ወ/ፍ/ቤት ሆኖ አመልካች ከሳሽ ሲሆኑ ከ1ኛ_4ኛ ያሉ ተጠሪዎች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡የክርክሩ ይዘት በአጭሩ አመልካች በቀን 12/12/2013

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ዓ.ም ያቀረቡት ክስ በካርታ ቁጥር 2048/2000 የሆነ በአዳማ ከተማ ጉሮ ቀበሌ በህጋዊ መንገድ የተሰጠኝ 105 ካሜ ይዞታ አለኝ፡፡ተጠሪዎች ይህን ይዞታዬን በቀን 25/8/2012 ዓም ይዘውብኝ ህንጻ ለመስራት በዝግጅት ላይ መሆናቸውን ስለተረዳሁ ያለህግ የያዙብኝን ይዞታዬን እንዲለቁልኝ ተብሎ እንዲወሰን የቀረበ ነው፡፡ተጠሪዎች በቀን 6/3/2014 ዓም መልስ ያቀረቡ ሲሆን፤1ኛ፤3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች አመልካች ባቀረቡት ይዞታ ላይ አንዳች ጥቅም ወይም መብት የሌለን በመሆኑ ልንከሰስ አይገባም ከክሱ እንድንወጣ በማለት ተከራከሩ፡፡

2ኛ በሰጡት መልስ የክርክሩ ይዞታ የአመልካች አይደለም፤ይዞታው በህጋዊ መንገድ አርሶ አደር በመሆኔ በካርኔ ቁ፤480078 በ2001 ዓም ከእርሻቸው የተፈናቀሉ አርሶአደሮች ለሚሰጥ የተሰጠኝ ነው፡፡ይህ ይዞታ መኖሪያ ቤት ለማግኘት ከፍዬ ስጠባበቅ ቆይቼ የመሬት አከፋፋይ ኮሚቴ በቀን 24/4/2012 ዓም በሰጠው ውሳኔ መሰረት የነበረኝ ካርታ ተለውጦ ስፋቱ 389.69 ካሜ የሆነ ባለ 5 ፎቅ እንድሰራ የተሰጠኝና ከድሮ ጀምሮ በእጄ ያለ ሳይት ፕላን ተሰጥቶኝ በእኔ ቁጥጥር ያለ ይዞታ እንጂ የአመልካች ይዞታ አይደለም በማለት ተከራከሩ፡፡

የስር ፍ/ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ ከመሬት አስተዳደር አጣርቼያለሁ በማለት ክርክር ያስነሳው ይዞታ የ2ኛ ተጠሪ መሆኑ ተረጋግጦዋል፡፡አመልካች ክሳቸውን በማስረጃ አላስረዱም በማለት ከዚህ ይዞታ መብት የላቸውም ብሎ የአመልካችን ክስ ውድቅ በማረግና ቦታው የሁለተኛ ተጠሪ ፍቃዱ ሀ/ማርያም ነው በማለት ወሰነ፡፡አመልካች በውሳኔው ቅር በመሰኘት እስከ ኦሮሚያ ክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ቅሬታ ቢያቀርቡም ፍ/ቤቶቹ የስር ውሳኔን አጽንተዋል፡፡

ይህ ፍ/ቤትም ለክርክሩ መነሻ የሆነው የመሬት የይዞታ በካርታ ቁጥር 2048/2000 በቀን 14/10/2005 ዓም በአመልካች ስም በህጋዊ መንገድ ተመዝግቦ እንደተሰጣቸው ባላከራከረበት ይህ ይዞታ በልዩ ኮድ ተካቶ በ2ኛ ተጠሪ ስም ተደርቦ በቀን 1/11/2013 ዓም ተመዝግቦ የተሰጠ መሆን አለመሆኑን እንዲሁም ካርታው ተደርቦ ተሰጥቶዋል የሚባል ከሆነ በአመልካች የይዞታ መብት ላይ የሚኖረው ህጋዊ ውጤት ምን ሊሆን ይገባል የሚለው በአግባቡ ተጣርቶ የተሰጠ ውሳኔ ነው ወይ? በአዋጅ ቁጥር 818/2006 አንቀጽ 43 ከተደነገገውና እና ከፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ222394 ያልታተመ ውሳኔ እና በሌሎች መዛግብት በተመሳሳይ ጉዳይ የተሰጠ የህግ ትርጉም የተከተለ መሆን አለመሆን በጭብጥነት በመያዝ የተፈጸመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖር ለመመርመር ያስቀርባል በማለት የግራ ቀኙ መልስ እና የመልስ መልስ በማስቀረብ አከራክሮዋል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክር ይዘት አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም የቀረበውን ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ፤በዚህ መዝገብ ከተያዘው ጭብጥ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ህጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሯል። አመልካች ከመሰረቱ ቦታው ካርታ ተሰጥቶኝ በይዞታ ማረጋገጫ የያዝኩት ቦታ ነው በማለት ነው የሚከራከሩት።ስልጣን ካለው አካል ለቦታው ማስረጃ አልተሰጣቸውም የተባሉም አደሉም። አመልካች የይዞታ ባለመብትነት ማስረጃ ከከተማው አገኘሁ የሚሉት በ2005 አ.ም ሲሆን፤ ሁለተኛ ተጠሪ ደግሞ ማስረጃ ተሰጣቸው የሚባለው ከ8 አመት በኋላ በ2013 አ.ም ነው። አመልካች ቦታው ተወስዶባቸው ለመሬት ባንክ የገባም አደለም።

የወረዳው ፍርድ ቤት ለሶስት ግዜ ከተለያዩ ከመሬት አስተዳደር መስርያ ቤቶች ስለይዞታው አጣርቼ የሁለተኛ ተጠሪ መሆኑን አረጋግጫለሁ በማለት ነው ይዞታው የሁለተኛ ተጠሪ ነው በማለት የወሰነው።ሶስት ግዜ አደረግኩት የሚለውን ማጣራት ስንመለከተው፤ በመጀመርያው ማጣርያ ላይ የከተማው በተለያየ እርከን ያሉ ሶስት መስርያ ቤቶች በአንድ ላይ እንዲያጣሩ እንዳዘዘ መዝገቡ ያሳያል። እነዚህም ሶስት አካላት የአዳማ ከተማ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት፤የቦሌ ክ/ከ/መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት እና የጎሮ ቀበሌ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ናቸው። እነዜህ መሬቱ በሚገኝበት የሚገኙ ከላይ እስከታች ያሉ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መስርያ ቤቶች በአንድላይ አጣርተው ውጤት እንደገለጹ መዝገቡ ይናገራል።

ከላይ በገለጽነው በመጀመርያው ማጣራት የተገለጸውን ስንመለከተው፤ክርክር ያስነሳው ቦታ ለአመልካች የተሰጠ መሆኑን፤ካዴስተር ሲገባ ካርታው ተቀይሮ ለሁለተኛ ተጠሪ ፍቃዱ ሀ/ማርያም የተሰጠ መሆኑን ይገልጻል በማለት ፍርድ ቤቱ በግልጽ አስፍሮታል። ይህ በግልጽ የተጣራ ሆኖ እያለ ፍርድ ቤቱ እንደገና በጥልቀት አጣራለሁ በማለት ለከተማው መሬት አስተዳደርና ለምስራቅ ሸዋ ከተማ መሬት አስተዳደር አዘዝኩ በማለት ቦታው የ2ኛተጠሪ ነው ብለው ምላሽ ሰጡን ይላል።በአመልካች ጠበቃ አቤቱታ ለ3ኛ ግዜ የኦሮሚያ መሬት ጽ/ቤት አጣርቶ የአመልካች ካርታ ኮርዲኔትና አዋሳኝ የለውም ተብሏል በማለት እንደወሰነ ከመዝገቡ ለማረጋገጥ ችለናል።

ፍርድ ቤቱ መጀመርያ ባደረገው ማጣራት አከራካሪው ቦታ ለአመልካች የተሰጠ የነበረ ስለመሆኑና፤ካደስተር ሲገባ ለሁለተኛ ተጠሪ ተቀይሮ የተሰጠ ስለመሆኑ ግልጽ ማስረጃ መጥቶለታል።ይህን ማስረጃ የሰጡት ደግሞ ከአከራካሪው ቦታ ማስረጃ አሰጣጥ ጋር ተያይዞ የበለጠ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ቅርበት ያላቸው ሶስት ጽ/ቤቶች በአንድ ላይ አጣርተውና ለይተው ነው፡፡ይህን ማጣራት በማለፍ ፍርድ ቤቱ የከተማው መሬት አስተዳደርንና የምስራቅ ሸዋ መሬት ጽ/ቤትን በጥልቀት አጣራለሁ ብሎ ማዘዙ ምክኝያታዊነት አላገኘንበትም፡፡ ሁለተኛ ማጣራጥ የተባለው ውጤት ሲቀርብ የአመልካች ጠበቃ ባቀረቡት ቅሬታ ላይ ተመስርቼ ለኦሮሚያ መሬት ጽ/ቤት አዘዝኩ የሚለው ሶስተኛ ማጣርያም ሁለተኛው ማጣርያ አለምክንያት በመታዘዙ የመጣ ጉዳይ ነው፡፡ የመጀመርያው ማጣርያ በቂና አሳማኝ ማስረጃ ሰጥቶ የነበረ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በኂላ ታዘው ቀረቡ የተባሉት ማስረጆችም ቢሆን ለአመልካች ከሁለተኛ ተጠሪ አስቀድሞ ካርታ አልተሰጠም የሚሉ አደሉም፡፡ የመጨረሻው ማጣርይ የአመልካች ካርታ ኮርዲኔትና አዋሳኝ አያሳይም ብሏል መባሉ እንደተጠበቀ ሆኖ፡፡

በእኛ በኩል ግን በመጀመርያው ማጣርያ የቀረበው ማስረጃ ነገሩን ግልጽ ያረገና ለይዞታውና ለማስረጃው አሰጣጥ ቅርብ የሆኑና በአግባቡ ስለማስረጃውና ስለቦታው በቂ መረጃ ያላቸው አካላት በአንድላይ ተቀናጅተው የሰጡት ማስረጃ በመሆኑ በዚህ ማስረጃ ላይ ለውሳኔ አሰጣጥ በዋናነት መመስረት ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡በዚህ ማስረጃ ቦታው ለአመልካች የተሰጠ እንደሆነ በኂላ ተቀይሮ ለሁለተኛ ተጠሪ እንደተሰጠ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ተቀይሮ የሚለው አነጋገር ግን ለአመልካች ሌላ ቦታ ተሰጥቶ መሆኑን በግልጽ አያመለክትም፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ አመልካች ህጋዊ ካርታ እያላቸው ተደርቦ ለሁለተኛ ተጠሪ መሰጠቱን ነው የሚያሳየው፡፡

የከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባ አዋጅ ቁጥር818/2006 አንቀጽ 42ተቃራኔ ሁኔታ መኖሩ እስካልተረጋገጠ ለመሬት ተጠቃሚነት የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት የተሰጠው ሰው የመሬቱ ባለይዞታ ነው ይላል፡፡ የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 43 ደግሞ ሁለት ወይም ከዝያ በላይ ሰዎች በአንድ ባለይዞታ ሊመዘገብ የሚገባን መብት ካገኙ በመጀመርያ የተመዘገበው ቅድምያ ይሰጠዋል ይላል፡፡ አመልካች በዚህ ይዞታ ላይ ካርታ ያገኙት ስልጣን በሌለው አካል ስለመሆኑም ሆነ መብታቸውን ሊያሳጣ የሚችል ሌላ ተቃራ ሁኔታ አላገኘንም፡፡በሌላ በኩል አመልካች በይዞታው ላይ ማስረጃና መብት ያገኙ መሆኑም ግልጽ ነው፡፡በመሆኑም በዚህ መዝገብ በክልሉ ፍርድ ቤቶች በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመ ሆኖ ስላገኘነው ከዚህ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

- በአዳማ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤትበመ/ቁ37638 በግንቦት 26/2014 ኢ.ም የተወሰነውንና በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ40312 በሀምሌ12/2014፤በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 401238 በጥቅምት 17/2015፤በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ420757 በጥር 17/2015 ኢ.ም የጸናውን ውሳኔ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ348(1) መሰረት ሽረነው አመልካች ክርክር ያነሱበት 105 ካሬሜትር ይዞታ ላይ ባለመብት ናቸው ብለን ወስነናል፡፡
- የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ ይቻቻሉ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፍ/ደ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
## የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መ/ቁጥር 245961

ጥቅምት 06 ቀን 2017 ዓ/ም

ዳኞች - ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻዉ አዳነ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሰናይት አድነዉ

ሀፊዝ አባጀማል

አመልካች ፡- የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር

ተጠሪ ፡- 1. ኃ/ገብርኤል ፍልፍሉ

2. ሰንሻይን ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር

መዝገቡ ተመርምሮ ተከለታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል።

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ የጉዳት ካሳን የሚመለከት ነዉ። ክርክሩ የተጀመረዉ በአማራ ክልል የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁን 1ኛ ተጠሪ ባቀረቡት ክስ ሲሆን የአሁን አመልካች 1ኛ ተከሳሽ፤ 2ኛ ተጠሪ ደግሞ 2ኛ ተከሳሽ ነበሩ።

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው 1ኛ ተጠሪ ባቀረቡት ክስ በስሜ ተመዝግቦ የተሰጠኝን ስፋቱ 2.6276 ሄክታር የሆነዉን የእርሻ መሬት ላይ አመልካች ለ2ኛ ተጠሪ በሰጠዉ ዉል መሰረት ለሚሰራዉ የአስፓልት መንገድ ከ2012 ዓ/ም ጀምሮ ለገረጋንቲ ማዉጫነት በመጠቀም ከመሬት በታች ከ 7 ሜትር በላይ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ወደ ዉስጥ በመቆፈሩ መሬቱ ሙሉ ለሙሉ ለእርሻ አገልግሎት በማይዉልበት ደረጃ ያለ እና ዘላቂ ጉዳት የደረሰበት በመሆኑ የበልግ እና መህር ሰበል ግምት፣ የመሬት ቋሚ ማሻሻያ እና የተረፈ ምርት ካሳ ጠቅላላ ብር 5,700,000.00 (አምስት ሚሊዮን ስባት መቶ ሺ) አመልካች እና 2ኛ ተጠሪ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠጥቀዋል።

አመልካች በቀረበዉ ክስ ላይ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበ ሲሆን ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ በሰጠው መልስ ለአሁን 2ኛ ተጠሪ ከ1ኛ ተጠሪ መሬት ጎን ያለን የእርሻ መሬት ለገረጋንቲ ማዉጫነት እንዲጠቀም ግምቱ ተሰርቶ አስረክበን የነበር ቢሆንም ይህ መሬት ዉሃ ያወጣል በማለት 2ኛ ተጠሪ ከአመልካች እዉቅና ዉጭ የ1ኛ ተጠሪ የእርሻ መሬት ላይ የግምት ስራ ሳይሰራ ቦታዉ በወረዳዉ ተለክቶ ከተያዘ እና ገረጋንቲ መመረት ከጀመረ በኃላ ዘግይቶ ክስም ከቀረበ በኃላ ጉዳዩን አሳዉቆናል፤ ስለሆነም የ1ኛ ተጠሪ የእርሻ መሬት በትክክል መወሰዱ የተረጋገጠ እና የተወሰደዉም ለግዜአዊ አገልግሎት በመሆኑ የፕሮጀክቱ ስራም ያላለቀ እና በሚመለከተዉ አካል የእርሻ መሬቱ ወደነበረበት መመለስ አለመመለሱ ያልተረጋገጠ በመሆኑ 1ኛ ተጠሪ የጠየቀዉ ዘላቂ ጉዳት ካሳ ዉድቅ ሆኖ በግዜአዊ የፕሮጀክቱ ቆይታ መሰረት በሚመለከተዉ አካል ተጣር በሚቀርበዉ ግምት የካሳ ከፍያዉን ፈፅመን 2ኛ ተጠሪ ላይ የከፈልነዉን ክፍያ እንድናስመልስ ይወሰንልን በማለት መልስ ሰጥቷል።

2ኛ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች ለገረጋንቲ ማምረቻ ያስረከበን የእርሻ መሬት ዉሃማ በመሆኑ እና የሚፈለገዉ ገረጋንቲ የ1ኛ ተጠሪ የእርሻ መሬት ላይ የተገኘ በመሆኑ ለአመልካች ወኪል እና መንገድ ስራዉን ለሚቆጣጠረዉ ኮር ኮንሳልቲንግ ኢንጂነር በቃል አሳዉቀን ቦታዉ በወረዳ ከተለካ በኃላ የፁሁፍ ስራዉ ሳያልቅ ገረጋንቲ ማምረት የጀመርን ሲሆን ጉዳዩ እልባት ሳያገኝ ኮንሳልቲንግ ኢንጂነሩ የዉል ግዜዉ የተጠናቀቀ በመሆኑ ጉዳዩ በእንጥልጥል ቀርቷል፤ የተመረተዉ ገረጋንቲ ለመንገድ ስራ የዋለ በመሆኑ የ1ኛ ተጠሪ የካሳ ጥያቄ በወረዳዉ ተለክቶ ግምቱ እየተሰራ በመሆኑ ግምቱ ከተሰራ በኃላ ካሳ የመክፈል ግዴታ የአመልካች በመሆኑ ልንጠየቅ አይገባም። ከሳሽ የፕሮጀክቱ ስራ ባላለቀበት ሁኔታ እና ስራዉ ተጠናቆ በባለሙያ የእርሻ መሬቱ ለወደፊት ምርት ይሰጣል አይሰጥም የሚለዉ ሳይረጋገጥ የጠየቁት ዘላቂ ካሳ እና ግምት የማስረጃ ድጋፍ የሌለዉ በመሆኑ ዉድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል።

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቀረበዉን መጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በብይን ዉድቅ አድርጎ የግራቀኙን ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ 2ኛ ተጠሪ ለሚሰራዉ የመንገድ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ስራ የ1ኛ ተጠሪን የእርሻ መሬት ለግንባታ የሚዉል ግብአት ለማዉጣት የተጠቀመበት ስለመሆኑ የተረጋገጠ እና የታመነ ጉዳይ ነው፤ ይህንን ይዘታ ለአገልግሎት ሲያዉሉ ተገቢዉ ካሳ ያልከፈለ መሆኑም የታመነ በመሆኑ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 40 እና በአዋጅ ቁጥር 1161/2011 መሰረት ለ1ኛ ተጠሪ ካሳ ሊከፈል የሚገባ በመሆኑና አመልካች ካሳ ለመክል ኃላፊነቱን እወስዳለሁ በማለት መልስ የሰጠ በመሆኑ አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ ካሳ የመክፈል ኃላፊነት አለበት። የመሬቱን የማልማት ሁኔታ በተመለከተ የባሶና ወራና የመሬት አስዳደር ባለሙያ በቁጥር ባወገመአአ/662/30 በቀን 20-10-2014 ዓ/ም በጻፈው ደብዳቤ በአጭር ግዜ ዉስጥ አገግሞ ጥቅም በማይሰጥ መልኩ ለምነቱን ያጣ በመሆኑ ጉዳቱ ዘላቂ ጉዳት ነዉ በማለት የገለፀ በመሆኑ በተረጋገጠዉ የዘላቂ ጉዳት ካሳ ግምት መሰረት አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ ብር 3,560,395.25 (ሶስት ሚሊዮን አምስት መቶ ስልሳ ሺ ሶስት መቶ ዘጠና አምስት ከ25/100) ሊከፍል ይገባል በማለት ዉሳኔ ሰጥቷል።

አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝቶ ይግባኝ ለአማራ ብ/ክ/መ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ይግባኙ በፍብ/ስ/ስ/ሀ/ቁ 337 መሰረት ተሰርዟል።

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው። አመልካች ሚያዚያ 19/2015 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር ማመልከቻ በውሳኔው ተፈፀመ የሚለውን መሠረታዊ የሕግ ስሕተት በመዘርዘር እንዲታረምለት ጠይቋል። የማመልከቻው ይዘት ባጭሩ የ1ኛ ተጠሪ የእርሻ መሬት ለግዜአዊነት የተወሰደ በመሆኑ የፕሮጀክት ስራዉ ተጠናቆ በእርሻ መሬቱ ላይ ለም አፈር ተሞልቶ ለምነቱ ተመልሷል አልተመለሰም የሚለዉ በባለሙያ ሳይረጋገጥ ኮንትራክተሩ መሬቱን በግዚአዊነት የወሰደበት ግዜ ሳያበቃ በእይታ ብቻ የመሬቱ ለምነት ሊመለስ አይችልም ተብሎ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢነት የሌለዉና የካሳ አዋጁን የሚጣረስ በመሆኑ ሊታረም ይገባል። በቦታዉ ላይ የሚሰራዉ ስራ አለመጠናቀቁን አሁን ድረስ አፈር እየተወሰደ ለግንባታ ስራዉ እየዋለ ያለ ለመሆኑ ባቀረብነዉ ምስክር አረጋግጠን እያለ የስር ፍርድ ቤት የ1ኛ ተጠሪን ምስክሮች ቃል ብቻ በመያዝ በባለሙያ አረጋግጫለሁ በማለት ዘላቂ ጉዳት ደርሷል ሲል የደረሰበት መደምደሚያ ተገቢነት የለውም። ከ1ኛ ተጠሪ ዉጭ ሌሎች ሁለት አርሶ አደሮች በተመሳሳይ በሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ላይ ክስ አቅርበዉ ሊከፈል የሚገባዉ ግዜአዊ ካሳ ነዉ ተብሎ ተወሰኖ እያለ ጉዳዩ ተመሳሳይ እና ለጉዳዩ የቀረቡት ምስክሮችም ተመሳሳይ ሆነዉ ሳለ በዚህ ጉዳይ ዘላቂ የጉዳት ካሳ ክፈሉ ተብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት የታየበት በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ያሳለፉት ውሳኔና ትዕዛዝ ይታረምልን በማለት ጠይቋል።

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ቅሬታው ተመርምሮ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ ዘላቂ የጉዳት ካሳ እንዲከፍላቸዉ የወሰነዉ በ1ኛ ተጠሪ የእርሻ መሬት ላይ የደረሰዉ ጉዳት ዘላቂ መሆኑን አረጋግጦ መሆን አለመሆኑን አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ጉዳዩ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 28(3) መሰረት እና ይህን ለማስፈፀም በወጣዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስነስርአት መመርያ ቁጥር 17/2015ዓ/ም አንቀፅ 7(2) መሰረት ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል።

1ኛ ተጠሪ ሐምሌ 27 ቀን 2015 ዓ/ም ባቀረቡት መልስ 2ኛ ተጠሪ የእርሻ መሬቱን ለገረጋንቲ ድንጋይ ማዉጫ መጠቀሙ እና ከአመልካች እዉቅና ዉጭ የወሰደ መሆኑ ያልካደ ሲሆን የፕሮጀክት ስራዉ የተጠናቀቀ እና በእርሻ መሬቱ ላይ የደረሰዉ ጉዳት ዘላቂ መሆኑን በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ  እና አመልካች መሬቱን በግዜአዊነት ስለመዉሰዱ፣ ስለ መሬቱ ማገገም እና አለማገገም እንዲሁም የመሬቱን አመላለስ በተመለከተ ዉል የሌለዉ በመሆኑ እንዲሁም አመልካች መሬቱ ወደ ነበረበት የለምነት ደረጃ እንዲመለስ ምንም ጥረት ያላደረገ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ዘላቂ የጉዳት ካሳ እንዲከፈል መወሰኑ የህግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ ዉሳኔው ሊፀና ይገባል ብለዋል።

2ኛ ተጠሪ በበኩል ሐምሌ 26 ቀን 2015 ዓ/ም በተፃፈ መልስ ክርክር የተነሳበት ቦታ የ1ኛ ተጠሪ ሲሆን በቦታዉ ላይ የሚገኘዉ ገረጋንቲ 2ኛ ተጠሪ ለመጠቀም ጠይቆ ከአመልካች የተሰጠዉ ሲሆን ስራዉ እስኪጠናቀቅ ላለዉ ግዜ በግዜአዊነት የተወሰደ በመሆኑ ግዜአዊ ካሳ ተስርቶላቸዋል፤ ስራዉ ያልተጠናቀቀ በመሆኑ እስከ አሁን ቦታዉ ላይ ገረጋንቲ እየወጣ ለመንገድ ስራዉ እየዋለ በመሆኑ በመሬቱ ላይ ዘላቂ ጉዳት መድረሱ የሚረጋገጠዉ የመንገድ ስራዉ ተጠናቆ ቦታዉ ላይ አፈር ተሞልቶ መሬቱ ወደ ቀድሞ ይዘታዉ ይመለሳል አይመለስም የሚለዉ በባለሙያ ሲረጋገጥ ብቻ እንጂ ከወዲሁ የደረሰዉ ጉዳት ዘላቂ ነዉ ማለት ስለማይቻል ስራዉ ሳይጠናቀቅ የደረሰዉ ጉዳት ዘላቂ ነዉ በሚል ካሳ እንዲከፈላቸዉ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ዘላቂ ካሳ ሊከፈል አይገባም ተብሎ ይወሰን በማለት የአመልካችን ቅሬታ ደግፎ ተከራክሯል።

አመልካች ተጠሪዎች ባቀረቡት መልስ ላይ የመልስ መልስ በማቅረብ ቅሬታዉን አጠናክሯል። መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረው በዚህ ሁኔታ ነው። በበኩላችን በሰበር ችሎቱ የተያዘውን ጭብጥ ከግራቀኙ ክርክር እና ተገቢነት ካላቸው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማያያዝ መርምረናል።

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40(4) መሠረት አርሶ አደሮች ከመሬታቻው ያለመፈናቀል መብት ያላቸው መሆኑና አፈፃፀሙን በሚመለከት በህግ እንደሚወጣ ያመለክትል። ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት

*ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !*

ይዞታ የሚለቀቅበትንና የንብረት ካሣ የሚከፈልበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር በአዋጅ ቁጥር 1161/2011 ለህዝብ ጥቅም ሲባል አግባብ ባለው የመንግስት አካል ውሳኔ ሲተላለፍ በአዋጁ መሠረት ካሣ ተከፍሎ መሬቱን የማስለቀቅ/የመጠቀም ሥልጣን ለመንግስት አካላት ይሰጣል፡፡ የሚከፈለው ካሣም መሬቱን በግዜያዊነት ወይም በቋሚነት የሚለቀቅ መሆኑን መሰረት በማድረግ በመሬቱ ላይ ለሚገኘው ንብረት እና በመሬቱ ላይ ለተደረገው ቋሚ መሻሻል ፤ እንዲሁም ይዞታውን በግዜያዊነት/በቋሚነት እንዲለቅ በመደረጉ የሚከፈል ካሳ ሁሉ ስለመሆኑ ከአዋጁ ዝርዝር ድንጋጌ መረዳት ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ለሚሰራዉ የመንገድ ስራ የ1ኛ ተጠሪ የእርሻ መሬት ለግንባታ የሚዉል ግብአት ለማዉጣት ጥቅም ላይ እየዋለ መሆኑ፤ እንዲሁም ይዞታው ለአገልግሎት ሲውል ለ1ኛ ተጠሪ ተገቢዉ ካሳ ያልከፈለ መሆኑም አከራካሪ አልሆነም፡፡ ይልቁንም አከራካሪ ሆኖ እስከዚህ ፍርድ ቤት የዘለቀው ከሳሽ መሬቱ ሙሉ ለሙሉ ለእርሻ አገልግሎት በማይዉልበት ደረጃ ደርሷልና ዘላቂ ጉዳት ተብሎ ሊወሰድ ይገባል በሚል በዚሁ አግባብ የዘላቂ ጉዳት ካሳ አስልተው የጠየቁ ሲሆን ተከሳሾች በበኩላቸው ይዞታው የተወሰደዉ ለግዜአዊ አገልግሎት መሆኑን፤ የፕሮጀክቱ ስራም ያላለቀ እና በሚመለከተዉ አካል የእርሻ መሬቱ ወደነበረበት መመለስ/አለመመለሱ ያልተረጋገጠ መሆኑን በመጥቀስ ዘላቂ ጉዳት ካሳ ሊወሰን እንደማይገባ ተከራክረዋል፡፡

ግራቀኙ በዚህ አግባብ ቢከራከሩም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመሬቱን የመልማት ሁኔታ በተመለከተ የመሬት አስተዳደር ባለሙያ በአጭር ግዜ ዉስጥ አገግሞ ጥቅም በማይሰጥ መልኩ ለምነቱን ያጣ መሆኑን ገልጿል በሚል ምክንያት ብቻ ጉዳቱን ዘላቂ ጉዳት ነዉ በማለት አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ ብር 3,560,395.25 (ሶስት ሚሊዮን አምስት መቶ ስልሳ ሺ ሶስት መቶ ዘጠና አምስት ከ25/100) እንዲከፍል ወስኗል፡፡

በመሠረቱ ፍርድ ቤት በሕግ ጥበቃ የተደረገለት መብት ተጥሶ ሲገኝ የሚቀርበውን ዳኝነት አይቶ በሕግ እውቅና የተሰጠውን መብት የማስከበር ኃላፊነት ያለበት ሲሆን በሕግ ያልተሰጠን መብት ግን የሚላግስ ውሳኔ እንዲሰጥ አይጠበቅም፡፡ 1ኛ ተጠሪ በሕጋዊ መንገድ ከያዙት ይዞታ መሬታቸው ያለመነቀል ህገ መንግስታዊ መብት ያላቸው በመሆኑ ፤ መሬቱ በህጉ አግባብ ለሕዝብ ጥቅም ተብሎ ሲወሰድና ዘላቂ ጉዳት መድረሱ ሲረጋገጥ ከፍሲል በተጠቀሰው አዋጅ እና ማስፈፀሚያ ደንቡ የተመለከተውን ካሣ የማግኘት መብት አላቸው፡፡ በአንጻሩ ይዞታው የተወሰደዉ ለግዜአዊ አገልግሎት ከሆነና የፕሮጀክቱ ስራም ካላለቀ እንዲሁም በህጉ በተመለከተው ተገቢ አካል የእርሻ መሬቱ ወደነበረበት መመለስ/አለመመለሱ ካልተረጋገጠ ፍርድ ቤቱ የዘላቂ ጉዳት ካሳ ሊወስን የሚችልበት የህግ አግባብ አይኖርም፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካች ካሳ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት ያሳለፉት ውሳኔ የሚነቀፍ ባይሆንም የከሣ ስሌቱን በተመለከተ ግን ውሳኔ የተሰጠው ይዞታው ለግዜአዊ አገልግሎት መወሰድ አለመወሰዱን፤ ተገቢው አካልም የእርሻ መሬቱ ወደነበረበት መመለስ/አለመመለሱን እንዲያረጋግጥ ሳይደረግ እና በአጠቃላይ በመሬቱ ላይ ያለው ሁኔታ በሕጉ ላይ በተመለከተው አግባብ ተጣርቶ ባለመሆኑ ጉዳቱ ዘላቂ ጉዳት ነዉ ተብሎ የዘላቂ ጉዳት ካሳ መወሰኑ የህግ ስህተት ነው ብለናል። ተከታዩንም ወስነናል።

**ው ሳ ኔ**

1. የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 0137441 ጥር 26 ቀን 2015 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የአ.ብ.ክ.መ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 0122300 መጋቢት 15 ቀን 2015 ዓ/ም የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ተሻሽሏል።
2. አመልካች ካሳ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት የተሰጠው ውሳኔ ፀንቷል።
3. ጉዳቱ ዘላቂ ጉዳት ነዉ ተብሎ ለዘላቂ ጉዳት ካሳ የተላለፈው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል።
4. የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተዘጋውን የመዝገብ በማንቀሳቀስ የ1ኛ ተጠሪ ይዞታ ለግዚያዊ አገልግሎት መወሰድ አለመወሰዱን፤ ተገቢው አካልም የእርሻ መሬቱ ወደነበረበት መመለስ/አለመመለሱን በማጣራት እንዲያረጋግጥ በማድረግ ለ1ኛ ተጠሪ ሊከፈል የሚገባውን የከሳ መጠን በህጉ አግባብ አጣርቶ ተገቢ ነው የሚለውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343(1) መሰረት መልሰናል። የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ።
5. የሰበር ክርክሩ ያስከተለው ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ።
6. በዚህ መዝገብ ላይ ተሰጥቶ የነበረው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል። ይጻፍ።

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

__ማስታወሻ፡-__ ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ሰ.መ.ቁ፡- 246474
ጥቅምት 06 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው
በዕውቀት በላይ
ቀነዓ ቂጣታ
ብርሃኑ መንግስቱ
ማርታ ተካ

አመልካች፡- ወ/ሮ ፋጡማ ከሊፋ ጠበቃ መሀመድ ሲራጅ ቀረቡ
ተጠሪዎች፡-1. ሀምዛ መስጅድ
2. አዳማ ከተማ መሬት አስተዳደር አጠቃቀም ፅ/ቤት / አልቀረቡም
መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥተዋል፡፡

**ፍርድ**

ለሰበር አቤቱታ መቅረብ ምክንያት የሆነው አመልካች በአዳማ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 39819 በቀን 13/06/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት ክርክር ያስነሳው ይዞታ ለአመልካች ይገባል በማለት የሰጠው ውሳኔ፣ የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 42089 በቀን 14/07/2015 ዓ.ም የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በመሻር መወሰኑም ሆነ በየደረጃው ያሉ ፍርድ ቤቶችም የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማጽናት ትእዛዝ መስጠታቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት የፈፀሙ በመሆኑ ታርሞ የአዳማ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲፀናላቸው ስላመለከቱ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ፡- የአሁን አመልካች በአዳማ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በተጠሪዎች ላይ ያቀረቡት ክስ በአዳማ ከተማ ጨፌ ቀበሌ ውስጥ ያለውን በቀድሞ ካርታ ቁጥር 6325/81 በቀን1/12/81 ላይ በወ/ሮ አስራት አያነው ስም ተሰጥቶ ተመዝግቦ የነበረው በቀን 23/7/1996 ላይ በተፈፀመ የሽያጭ ዉል ስምምነት በሰሜ ተመዝግቦ የሚገኘው በቋሚነት መጋዘን ቤት ያለበት በ1295 ካ.ሜትር ከሆነው ይዞታዬ ውስጥ 800 ካ/ሬ የሆነውን አዋሳኞቹ በክሱ ላይ የተገለፀው በቀን 19/10/2012 2ኛ ተከሳሽን በማጭበርበር የኢንዱስትሪ ሳይት ፕላን የሆነውን የካርታ ቁጥር 783/12፤ በቀን 19/10/2012ዓ.ም በማውጣት በይዞታዬ ላይ በጉልበት መስጅድ የገነቡ በመሆኑ የገነቡት መስጊድ

በራሳቸው ወጪ አፍርሰው እንዲያነሱ እና በህገ ወጥ መንገድ የወጣው ካርታ ይሻርልኝ እንዲሁም አመልካች ጠይቂ የነበረውን የዱቄት ፋብሪካ ኢንዱስትሪያል እና በዚህ ስፍራ ላይ የተከናወነውን ፕላን ጭምር ሰርቶ እንዲሰጠኝ እና አላስከፍልም ያለውን የመንግስት ግብር እንድከፍል ትእዛዝ በመስጠት ጭምር ይወሰንልኝ የሚል ዳኝነት መጠየቃቸው ያሳያል፡፡

የአሁኑ 1ኛ ተጠሪም በሰጡት መልስ ንብረቱ ህጋዊ በሆነ መንገድ ይዘን መጠቀም ከጀመርን ከ20 ዓመታት በላይ ሲሆን በዚህ ቦታ ላይ ለመጀመሪያ ግዜ ሀጂ ኑሩ አደም የተባለ ግላሰብ መስጅድ ገንብቶ ለአከባቢው ማህበረሰብ አገልግሎት ሲሰጥ ከቆየ በኋላ 674 ካ.ሜ ሸጠልን ሀምዛ መስጂድ ተብሎ እየተጠራ እስካሁን ድረስ ለአካባቢው ሙስሊም ማህበረሰብ አገልግሎት የሚሰጥ ቦታ ሆኖ ይህ መስጂድ ህጋዊ እውቅና በማግኘት በ2012 ውስጥ ቁጥሩ 785/12 የሆነ ህጋዊ ካርታ እና ፕላን አስወጥቶ ስልጣን ባለው የመንግስት አካል በኩል ፈቃድ የተሰጠው መሆኑን፤ መስጂዱ ሲገነባ የተቃወም ሰው አደለመኖሩን፤ አመልካች ያቀረቡት ካርታም የይዞታው አዋሳኝ የማይገልጽ መሆኑን፤ ካርታው ለአከራካሪው ይዞታ የተሰጠ ስለመሆኑ የሚያሳይ እንዳልሆነ፤ አመልካች በቀን 23/07/1996 ዓ.ም ገዝቻለሁ በማለት ያቀረቡት ማስረጀ ሀሰተኛ እንደሆነ ውሉም ስልጣን ባለው አካል ተረጋግጦ የተመዘገበ አይደለም፤ አመልካች በዚሁ ይዞታ እየተጠቀሙ የነበረ ስለመሆኑ የሚያስረዳ ማስረጃ የሌላቸው በመሆኑ ክሳቸው ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

በአሁኑ 2ኛ ተጠሪ በኩል የሰጠው መልስ፡- አመልካች ያቀረቡት የሽያጭ ውሉ የተፈፀመው እና ተረጋግጦዋል የተባለው የተለያየ ስለሆነ የህግ ሂደቱን ጠብቆ የተደረገ ውል አይደለም፤ ክርክር ያስነሳው ይዞታ የመንግስት ሆኖ ለ1ኛ ተጠሪ በህጋዊ መንገድ በካርታ ቁጥር 782/12 በቀን 19/10/2012 ዓ.ም 754 ካሬ የተሰጠ በመሆኑ ካርታው ሊሰረዝ አይገባም፤ የአመልካች ክስ ውድቅ ሊሆን ይገባል የሚል ነው፡፡

ክርክሩ በዚህ አግባብ የቀረበለት የአደማ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤትም የግራቀኙን ክርክርና ምስክሮች ሰምቶ እንዲሁም ከሚመለከታቸው አካላት በኮሚቴ ጉዳዩ እንዲጣራ ካደረገ በኃላ በመ/ቁ 39819 በቀን 13/06/2015 ዓ.ም ሲወስን፡- ለክርክሩ መነሻ የሆነው መሬት አመልካች በግዢ ያገኙት መሆኑ እና የሽያጭ ዉሉም ስልጣን ባለው አካል የተረጋገጠ በመሆኑ በአከራካሪው ይዞታ ላይ አመልካች መብት ያላቸው ስለመሆኑ የቀረቡት ማስረጃዎች እና ከወ/ሮ አስራት አያናው ማህደር መረዳት መቻሉን፤ በዚህ ይዞታ ላይ ካርታው በአመልካች ስም ባይሰራም ስፍራው ቦታውን ለንግድ አገልግሎት በሻጭ ስም ካርታው ተመዝግቦ እንደሚገኝ የሻጭ ማህደር የሚያሳይ መሆኑን፤1ኛተጠሪ ቦታው ሊይዙ የቻሉት ገዝተው ሳይሆን የአመልካች ባለቤት እንዲገለገሉበት የመስጅድ ቦታ ሲሰጡዋቸው ይዞታውን በማስፋፋት መያዛቸውን፤ 1ኛ ተጠሪ የግዢ እና የሽያጭ ዉል በሌለበት እና ሸጦልኛል ያሉት ሰው ሀጂ ኑር የተባለው ቀርቦ ሲመሰክር አለመሸጡን በግልፅ በመስከረበት ሁኔታ 2ኛ ተጠሪ 1ኛ ተጠሪ በዚሁ ይዞታ ላይ መብት ሳይኖረው በካርታ ላይ በድጋሚ ካርታ በመስራት ለ1ኛ ተጠሪ በህገ ወጥ መንገድ መብት የፈጠረ በመሆኑ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ይዞታ 1ኛ ተጠሪ እንዲለቁ እንዲሁም ለ1ኛ ተጠሪ የተሰጠ ካርታም እንዲሰረዝ ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡

1ኛ ተጠሪ በተሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘታቸው ይግባኝ ለአደማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም በመ/ቁ 42089 በቀን 14/07/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የግዥ ዉል

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የተደረገው በ1996 ዓ.ም ሆኖ እያለ የፀደቀው በ1988 መሆኑን ማስረጃው የሚያጠራጥር መሆኑን እንዲሁም ለአመልካች ሸጠዋል የተባሉት በወ/ሮ አስራት አያኖ በስማቸው የተሰጠው ካርታ ተሰርዞ ለ1ኛ ተጠሪ ካርታ ቁጥር 783/12 የተሰጣቸው መሆኑን በመግለፅ አከራካሪው ይዞታ ህጋዊ ባለይዞታ 1ኛ ተጠሪ በመሆኑ ይዞታው ለቀው ለአመልካች ሊያስረክብ አይገባም በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን ሽሮታል፡፡ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምስራቅ ኦሮሚያ ቋሚ ምድብ ችሎት በመ/ቁ 417334 በቀን 27/7/2015 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ያፀና ሲሆን የክልሉ ጠቅላ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 422920 በቀን 2/08/2015 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ትእዛዝ አጽንቷል፡፡
አሁን አመልካች በቀን 30/08/2015 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት ሰበር አቤቱታ ይዘቱ፡- አመልካች እየተቃወምኩ የመስጅድ ግንባታ ስለመከናወኑ በማስረጃ በተረጋገጠበት 1ኛ ተጠሪ ሊለቅ አይገባም በሚል ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት መወሰኑ ተገቢ አለመሆኑን፤ 1ኛ ተጠሪ በአመልካች ይዞታ ላይ ካርታ በስሙ ያሰራበት ስለሆነ ብቻ ህጋዊ ባለመብት የማያደርገው መሆኑን፤ አመልካች ቦታውን በህጋዊ መንገድ ከወ/ሮ አስራት አያና ከተባሉት ግለሰብ መጋቢት 23 ቀን 1996 ዓ/ም በተፈፀመ የቤት ሽያጭ ውል ገዝቼ ውሉ በክልሉ ፍትህ ቢሮ የተመዘገበና ከፀደቀ በኃላ አከራካሪው ይዞታ ለበርካታ ዓመታት ያህል በእውነት በእጄ በማድረግ እየተጠቀምኩበት የሚገኝ መሆኑን ባቀረቧቸው የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች ያስረዳሁና የስር ወረዳ ፍርድ ቤቱ ተረጋግጦ እያለና አመልካች ይህንኑ ይዞታ ጨምሮ የ30 አመት የሊዝ ክፍያ በመክፈል የ5 አመት የሊዝ ክፍያ ያልከፈሉት መኖሩን በሻጭ ስም ያለው ካርታ እንዲመክን የተደረገው ስመ-ንብረቱ ከሻጭ ገዢ ወደ ሆንኩት አመልካች ስም እንዲዞር ከተመራ በኃላ መሆኑን በማያሻማ መልኩ ተረጋገጠበት የዞኑ ከፍተኛው ፍርድ ቤት በማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬነገር ወደጎን በመተው 1ኛ አከራካሪው ይዞታ ባለመብት 1ኛ ተጠሪ ነው በሚል መወሰኑ ተገቢ አለመሆኑ፤ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቤት ሽያጭ ውሉ የተፈፀመበት ቀንና ውሉ በክልሉ የሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት የፀደቀበት ቀን ስህተት ያለበት ሆኖ ሲያገኘው የቀን ስህተቱ እንዴትና ለምን እንደተፈጠረ ሳያጣራና ሳይመረምር የፀደቀው የውል ሰነድ በቀድሞው የከተማው ማዘጋጃ ቤት የባህር መዝገብ ላይ ሰፍሮ የሚገኝ መሆኑን ማየት እየቻለ በደፈናው ሰነዱ የተጭበረበረ ነው ወደሚል መደምደሚያ መድረሱ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱና በየደረጃው ያሉት ሌሎቹ ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ/ትእዛዝ ተሽሮ የወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲፀላቸው ጠይቀዋል፡፡
ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የአመልካች አቤቱታ በመመርመር ለሰበር ቀርቦ ሊታይ የሚገባው ሆኖ ስላገኘው ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

1ኛ ተጠሪ በቀን 12/07/2016 ዓ.ም ጽፈው በሰጡት መልስ ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት አሁን በጭብጥነት የያዛቸው ፍሬ ነገሮች በሙሉ የማስረጃን ምዘና የሚመለከቱ እንደሆኑ፤ አመልካች ለክርክር መንስኤ የሆነውን ይዞታ በግዢ ስለማግኘታቸው በህጋዊ መንገድ ይዘው ሲጠቀሙበት ስለመቆየታቸው በስማቸው የተከፈተ ማህደር ስለመኖሩ እና ፍቃድና ካርታ ጭምር ተሰርቶ እንዲሰጣቸው ስለመጠየቃቸው በስማቸው የተረጋገጠ አንዳችም ነገር የለም፡፡የወረዳው ፍርድ ቤት ለዚህ ጉዳይ አግባብነት የሌለውን ማስረጃና ማህደር በመመርመር የማስረጃ አቀራረብና ምዘና ሒደቶችን በሚቃረን መልኩ ከ1988 ዓ/ም በፊት የነበረውን የእነ ወ/ሮ አስራት አያነው ማህደር እንደመረጃነት በፍርዱ ሀተታ ውስጥ መጥቀሱ ስህተት ነው፡፡ አመልካች ያቀረቡት ዉል ትክክለኛ አለመሆኑን በማረጋገጥ የዞን ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ አግባብ ነው፡፡ አከራካሪ ይዞታ ከ20 ዓመት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በፊት ከ1994 ጀምሮ በህጋዊ መንገድ አግኝቶ የህዝብ አገልግሎት መስጫ ሆኖ በመስጂድነት ሲያገለግል የቆየ ቦታውም በጨረቃና ሰነድ አልባ ይዞታ ይታወቅ ስለነበረ ሀጂ ኑሩ ከሚባል ሰው በግዢና በስጦታ ተገኝቶ ስንጠቀምበት የቆየን ነው፡፡ ካርታም የተሰጠን በህጋዊ መንገድ በመሆኑ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ መሆን አለበት በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

2ኛ ተጠሪ መጥሪያ የደረሰው መሆኑን ማረጋገጫ የቀረበ ቢሆንም መልስ ስላላቀረበ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡ አመልካች 1ኛ ተጠሪ በሰጡት መልስ ላይ የመልስ መልስ በማቅረብ ሰበር ክርክራቸውን በማጠናከር ተከራክሮዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን እኛም ከተያዘው ጭብጥ አንጻር የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመረነውም የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ፡- ክርክር ያስነውን ይዞታ ከወ/ሮ አስራት በግዥ ያገኑ መሆኑን ገልፀው ከፍቃዳቸው ውጭ 1ኛ ተጠሪ መስጂድ በመገንባት መያዛቸውን፤2ኛ ተጠሪም ለህግ አግባብ ውጪ ለ1ኛ ተጠሪ በዚሁ 800ካ.ሜ የሆነው ይዞታ ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ መስጠቱን ጠቅሰው 1ኛ ተጠሪ አዋሳኑ በክሳቸው የተጠሰው 800ካ/ሜ ይዞታ ላይ የገነቡት መስጂድ በራሳቸው ወጪ በማፍረስ እንዲያስረክቡ እንደሁም 2ኛ ተጠሪ ለ1ኛ ተጠሪ የሰጠው ካርታ እንዲሰረዝ ይወሰንልኝ የሚል ሲሆን 1ኛ ተጠሪ ደግሞ ይዞታውን የአመልካች የቀድሞ ባለቤት ከነበሩት ሀጂ ኑሩ ከሚባሉ ሰው በግዢና በስጦታ በማግኘት ለረዥም አመታት ስንጠቀምበት ከቆየን በኃላ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የተሰጠን ሲሆን አመልካች በቀን 23/07/1996 ዓ.ም ገዝቻለሁ በማለት ያቀረቡት ማስረጀ ሀሰተኛ ነው፡፡ ውሉም ስልጣን ባለው አካል ተረጋግጦ የተመዘገበ አይደለም፤ አመልካች በዚሁ ይዞታ እየተጠቀሙ የነበረ ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ የለም፤ በመሆኑም ክሳቸው ውድቅ ሊሆን ይገባል በሚል ሲከራከሩ በ2ኛ ተጠሪ በኩል አመልካች ያቀረቡት የሽያጭ ውሉ የተፈፀመው እና ተረጋግጦዋል የተባለው የተለያየ ስለሆነ የህግ ሂደቱን ጠብቆ የተደረገ ውል አይደለም፤ ለ1ኛ ተጠሪ የመንግስት ይዞታ በህጋዊ መንገድ በካርታ ቁጥር 782/12 በቀን 19/10/2012 ዓ.ም 754 ካሬ የሰጠ በመሆኑ ካርታው ሊሰረዝ አይገባም በሚል በስር ፍ/ቤት ተከራክረዋል፡፡

የአንድን ፍሬ ነገር መኖር ማስረጃ በማጣራትና በመመዘን የመወሰን ስልጣን ባለው የስር ወረዳ ፍርድ ቤት ኮሚቴ በማቋቋም ባደረገው ማጣራት ክርክር ያስነሳው ይዞታ ለወሮ አስራት አያነው ለኢንዱስትሪ አገልግሎት ተሰጥቶ ይዘው የቆዩት እና አመልካችም ከወ/ሮ አስራትና ከአቶ ፒፒያኖ በግዥ አግኝተውና ይዘው ሲጠቀሙበት መቆየታቸውን በስማቸው ማሕደር ተከፍቶ መስኩንም ወደ ዱቄት ፋብሪካ ለመቀየር ፍቃድና ካርታ ጭምር በስማቸው ሰርቶ እንዲሰጣቸው ጠይቀው በሂደት ላይ የነበሩ መሆኑን አረጋገጠዋል፡፡ ይዞታው ለመስጅድ አገልግሎት መዋል የጀመረው የአመልካች የቀድሞ ባለቤት የነበሩት ሀጂ ኑር በአከባቢው መስጅድ ባለመኖሩ ይዞታቸው ላይ ሲሰግዱ ሌሎች አብራዋቸው መስገድ በመጀመራቸው በሂደት ይዞታውን እየሰፋ መምጣቱን በስር በወረዳ ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ እንዲሁም 1ኛ ተጠሪ ክርክር ያስነሳውን ይዞታ በስጦታ እና በግዥ አግኝተናል ያሉ ቢሆንም የግዥ ውል የሌላቸው መሆኑን 1ኛ ተጠሪ ሸጡልኝ የሚላቸው ሀጂ ኑር የተባሉ ግለሰብ በችሎት ቀርበው ያልሸጡ መሆኑን መመስከራቸው ተረጋግጧል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

2ኛ ተጠሪ ለ1ኛ ተጠሪ የተሰጠው መሬት የመንግስት መሬት ነው በማለት መልስ የሰጡ ቢሆንም ክርክር ያስነሳው ይዞታ ቀድሞ የሚታወቀው በወ/ሮ አስራት አያናው መሆኑን በስማቸው ካርታ ቁጥር 362/81፣ በቀን ነሓሴ 01 ቀን 1981 ዓ.ም የተሰጣቸው መሆኑን እና ለወ/ሮ አስራት አያናው የተሰጠው ካርታ ባለበት በዚሁ ይዞታ ላይ በድጋሚ ለ1ኛ ተጠሪ ካርታ የሰጠ መሆኑም በስር ወረዳ ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡

የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመሻር አከራካሪው ይዞታ የ1ኛ ተጠሪ ነው በማለት ሲወስን ምክንያት ያደረገው አመልካች በሽያጭ ውል አገኘሁት የሚሉት ይዞታ ውሉ የተደረገው በ1996 ዓ.ም ሆኖ እያለ ውሉ በውል አዋዋይ ዘንድ የፀደቀው በ1988 መሆኑን ማስረጃው የሚያጠራጥር ነው እንዲሁም አመልካች የግል ማህደር የሌላቸው መሆኑን ለአመልካች ሸጥዋል የተባሉት ወይም በወ/ሮ አስራት አያኖ ስም የተሰጠ ካርታ የተሰረዘ ተሰርዞ ለ1ኛ ተጠሪ ካርታ ቁጥር 783/12 የተሰጣቸው መሆኑን በመግለፅ ነው፡፡ ሆኖም አመልካች ከሻጭ ጋር ያደረጉት ውል በክልሉ የሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት ቀርቦ የተመዘገና የፀደቀ ውል መሆኑ በስር ወረዳ ፍርድ ቤት በኮሚቴ ባደረገው ማጣራት የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ውል የተደረገበትና በውል አዋዋይ ፊት ቀርቦ የፀደቀበት ቀን የተለያየ ሆኖ ከተገኘም ውሉን ከመዘገበው አካል ውሉ ትክክለኛ መሆን አለመሆን ማጣራት እየቻለ በውል አዋዋይ ፊት ቀርቦ የተመዘገበ ውል ቀን ልዩነት በመኖሩ ብቻ ውሉ ህጋዊ አደለም ወደሚል ድምዳሜ ሊያደርስ የሚችል አይሆንም፡፡ በሌላ በኩል በስር ወረዳ ፍርድ ቤት አከራካሪው ይዞታ አመልካች በሽያጭ ያገኙት ስለመሆኑ በኮሚቴ ተቋቁሞ በተደረገው ማጣራት ተረጋግጧል፡፡ ሌላው በምክንያትነት የተጠቀሰው አመልካች ሸጠልኛል የሚሉት ሰው ተሰጥቶት የነበረው ካርታ በተሰረዘበት እና ይህ መሬት ሕጋዊ በሆነ መንገድ ለ1ኛ ተጠሪ ተሰጥቶ መስጅድ ሰርተውበት የያዙት ነው የሚል ነው፡፡

በመሠረቱ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40(1) ማንኛውም ኢትዮጵያ ዜጋ የግል ንብረት ባለቤት መሆን የተከበረለት/ላት መሆኑን ይደነግጋል፡፡ የሕገ መንግስቱ አንቀፅ 40(7) ድንጋጌም ማንም ኢትዮጵያዊ በጉልበቱ፣ ወይም በገንዘቡ በመሬቱ ላይ ለሚገነባው ቋሚ ንብረት ወይም ለሚያደርገው ቋሚ መሻሻል ሙሉ መብት እንዳለው፣ይህ መብትም የመሸጥ፣ የመለወጥ፣ የማውረስ፣ የመሬት ተጠቃሚነቱ ሲቋረጥ ንብረቱን የማንሳት፣ባለቤትነቱን የማዛወር ወይም የካሳ ክፍያ የመጠየቅ መብትን የሚያካትት እና ዝርዝር አፈጻጸሙም  በሕግ የሚወሰን መሆኑን ይደነግጋል፡፡ እንዲሁም አዋጅ 721/2004 ስር የከተማ መሬት በሊዝ ብቻ መያዝ ያለበት መሆኑን እና ከሊዝ ውጭ የከተማ ቦታ መያዝ የማይቻል መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

ሌላው በመሠረታዊነት የከተማ አስተዳደር ተፈጻሚነት ባላቸው ሕጎች መሠረት ይዞታን የማስተዳደር፣ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የመስጠትም ሆነ የመሰረዝ ስልጣን እንዳለው አከራካሪ አይደለም፡፡ የከተማው አስተዳደር ይህንኑ ስልጣኑን ተግባራዊ የሚያደርገውም በንብረቱ ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ማስረጃ እንዲሰጠው የሚጠይቀው ወገን ሕጋዊ ባለይዞታ መሆኑን በማረጋገጥ እና ይህንኑ በመመዝገብ ነው፡፡ በዚህ አግባብ ሕጋዊ ባለይዞታ መሆኑ ተረጋግጦ የይዞታ ማረጋገጫ ማስረጃ የሚሰጠው ባለይዞታም የዚሁ ንብረት ባለቤት እንደሆነ በህጉ ግምት የሚወሰድበት ስለመሆኑ ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1195 ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ የዚሁ ሕግ አንቀጽ 1196 ድንጋጌም ባለይዞታው የንብረቱ ባለቤት እንደሆነ በሕግ የሚወሰደውን ግምት ተቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ ሊስተባበል እንደሚችል ይደነግጋል፡፡
በያዝነው ጉዳይ አመልካች አከራካሪው ይዞታ ህጋዊ በሆነ ሽያጭ ውል ያገኙት ስለመሆኑ የስር ወረዳው ፍርድ ቤት ተረጋገጠ ሲሆን ውሉን ሲዋዋሉ አከራካሪው ይዞታ ስመሀብቱ በሻጭ ስም የነበረ

መሆኑን ውሉ ካደረጉ በኃላም ስመሀብት ወደስማቸው እንዲዞር በሂደት ላይ እያሉና በሻጭ ስም ካርታ እያለ 2ኛ ተጠሪ በዚሁ አከራካሪው ይዞታ ላይ በድጋሚ በ1ኛ ተጠሪ ስም ካርታ መስጠቱ በስር ወረዳ ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ፍሬነገር ሲሆን እዚህ ላይ መታየት ያለበት 2ኛ ተጠሪ ለ1ኛ ተጠሪ በዚሁ ይዞታ ላይ ካርታ የሰጠው በህጋዊ መንገድ መሆን አለመሆኑን ነው? 1ኛ ተጠሪ አከራካሪው ይዞታ የአመልካች የቀድሞ ባለቤት ከነበሩት ሀጂ ኑር የተባሉ ግለሰብ በፈቃዳቸው መጀመሪያ 200ካ.ሜ ላይ መስጂድ በመገንባት በግዢና በስጦታ ያገኙት ነው በሚል እየተከራከሩ ባሉበት 2ኛ ተጠሪ ደግሞ አከራካሪው ይዞታ የመንግስት እንደሆነና ለ1ኛ ተጠሪ በህጋዊ መንገድ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የተሰጠው መሆኑን በመግለጽ የሚያቀርቡት ክርክር 1ኛ ተጠሪ ይዞታውን አገኘን ከሚሉበት ምክንያት ጋር የማይጣጣም መሆኑን ያሳያል፤ በተጨማሪም 1ኛ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት በጽሁፍ በሰጡት መልሳቸው የሚከራከሩት አከራካሪው ይዞታ ሀጂ ኑሩ ከተባሉ በሽያጭና በስጦታ ያገኘነው ነው በሚል ቢሆንም ሀጂ ኑሩ የተባሉት በምስክርነት ቀርበው አከራካሪው ይዞታ ለ1ኛ ተጠሪ አለመሸጣቸውን መመስከራቸውን በስር ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ይህም ማለት ምንም እንኳ 1ኛ ተጠሪ አከራካሪው ይዞታ በሽያጭና በስጦታ ያገኘነው ነው በሚል ቢከራከሩም በዚህ አግባብ ያገኙት ስለመሆኑ ያቀረቡት ማስረጃ የለም በአንጻሩ ሸጡልን የሚልዋቸው ግለሰብም እንዳልሸጡ መመስከራቸው 1ኛ ተጠሪ አከራካሪው ይዞታ በህግ አግባብ የያዙት ስለመሆኑ አላስረዱም፡፡ 2ኛ ተጠሪም ቢሆን አከራካሪው ይዞታ የመንግስት የነበረ ይዞታ መሆኑን ጠቅሶ ቢከራከርም የመንግስት ይዞታ የነበረ ስለመሆኑ ያቀረበው ማስረጃ የለም፤ በ1ኛ ተጠሪ በኩልም ቢሆን ይዞታውን ከአመልካች ቀድሞ ባለቤት በስጦታና በሽያጭ አገኘን በሚል ተከራከሩ እንጂ የመንግስት ይዞታ የነበረ መሆኑና ከመንግስት በቀጥታ ያገኙት ስለመሆኑ ጠቅሰው ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ በአንድ ማስረጃ ይዘት ላይ በግልጽ የተመለከተዉን በአግባቡ ያላገናዘበ ዉሳኔ መስጠት ወይም በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠዉን ነጥብ ከሕጉ ጋር ሳያገናዝቡ መወሰናቸዉ ከተረጋገጠ እነዚህን ስህተቶች በሰበር ችሎት ማረም ማስረጃ ወደ መመዘን ዉስጥ ተገብቷል የሚያስብል ሳይሆን እንደመሰረታዊ የሕግ ስህተት ሊቆጠርና በሰበር ሰሚ ችሎት ሥልጣን ማእቀፍ ዉስጥ ታይቶ ሊታረም ይገባል ሲል ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 44804 (ቅጽ 11 ላይ እንደታተመዉ) ፣211615 (ያልታተመ)፣229926 (ያልታተመ) እና በሌሎች መዛግብት ላይ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

በስር ወረዳው ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረቡት የሽያጭ ውል ህጋዊነት ጭምር በኮሚቴ እንዲጣራ በማድረግ በፍሬነገር ደረጃ ክርክር ያስነሳውን ይዞታ ጨምሮ 1,295 ካሬ ሜትር ይዞታ በካርታ ቁጥር 3625/81 ነሐሴ 01 ቀን 1981 ዓ.ም ለወ/ሮ አስራት አያነው ለኢንዱስትሪ አገልግሎት ተሰጥቶ ይዘው የቆዩት እና አመልካችም ከወ/ሮ አስራትና ከአቶ ጆባኒ ፒፒያኖ በግዥ አግኝተዉና ይዘው ሲጠቀሙበት መቆየታቸዉን፣በስማቸው ማህደር ተከፍቶ መስኩንም ወደ ዱቄት ፋብሪካ ለመቀየር ፍቃድና ካርታ ጭምሮ በስማቸው ተሰርቶ እንዲሰጣቸው ጠይቀዉ በሂደት ላይ የነበሩ መሆኑን ተረጋግጦ እያለ፤ እንዲሁምይዞታው መስጅድ አገልግሎት መዋል የጀመረውም የአመልካች የቀድሞ ባለቤት የነበሩት ሀጂ ኑር በአከባቢው መስጅድ ባለመኖሩ በይዞታቸው ላይ ሲሰግዱ ሌሎችም አብረዋቸው መስገድ በመጀመራቸው በሂደት 1ኛ ተጠሪ እያስፋፉ መምጣታቸውን የ1ኛ ተጠሪ ምስክሮች ሳይቀሩ በሀጂ ኑር የተፈቀደው 200 ካ/ሜትር ሆኖ 1ኛ ተጠሪ በግዥ 647 ካ/ሜትር ጨመርን በሚል የ1ኛ ተጠሪን የይዞታውን አያያዝ ስለመግለጻቸው በማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬነገር የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይህንኑ በስሩ ባለው ፍርድ ቤት የተረጋገጠውን ፍሬነገር ወደጎን በመተው 1ኛ ተጠሪ በአከራካሪው ይዞታ ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ስላላቸው ህጋዊ ባለይዞታ ናቸው በሚል ምክንያት ብቻ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በህጋዊ መንገድ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ስለማግኘታቸው ባልተረጋገጠበት ሁኔታ 2ኛ ተጠሪ በሻጭ ስም የነበረውን ካርታ በማምከን ለ1ኛ ተጠሪ ይዞታውን መፍቀዱና የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ መስጠቱም ሆነ የቀድሞ ባለይዞታና በሽያጭ ዉል ያስተላለፉት ወ/ሮ አስራት የክርክሩ ተካፊይ ባልሆኑበትና ምንም ዓይነት ክርክር ባላነሱበት የአመልካችን የንብረትና የባለይዞታነት ሕገ -መንግስታዊ መብት በሚጋፋ መልኩ በግዥ ዉልና ለይዞታው አያያዛቸው ዕዉቅና በመንፈግ፤ 1ኛ ተጠሪ በአከራካሪው ይዞታ ላይ ህጋዊ ባለይዞታ በመሆኑ ሊለቅ አይገባም በ2ኛ ተጠሪ የተሰጠው ይዞታ ማረጋገጫ ካርታም ሊሰረዝ አይገባም በማለት የወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ በመሻር መወሰኑም ሆነ በየደረጃው ያሉት ፍርድ ቤቶችም ይህ የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ በማረም ሲገባቸው በማጽናት የሰጡት ትእዛዝ መሰረታቂ ማስረጃ ምዘና መርህን በሚጥስ መልኩ መወሰናቸው ስለሚያሳይ የፈፀሙት መሰረታዊ የሕግ ስህተት ሊታረም የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የስር ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ በማስረጃ ስለመረጋገጡ በውሳኔው ካሰፈረው ፍሬነገር አንጻር ሲታይ አመልካች በግዢ ካገኙት ቤትና ይዞታ ውስጥ በ1ኛ ተጠሪ ስለመያዙ ከተረጋገጠው 754ካ.ሜ ውስጥ 200ካ.ሜ በአመልካች የቀድሞ ባለቤታቸው ፍቃድ የተያዘ መሆኑ መረጋገጡ ከዚህ ውጪ ያለው 1ኛ ተጠሪ በማስፋፋት መያዛቸውን በማስረጃ የተረጋገጠ ፍሬነገር ሆኖ እያለ አመልካች በቀድሞ ባለቤታቸው ፈቃድ ስለመያዙ የተረጋገጠውን 200ካ.ሜ 1ኛ ተጠሪ እንዲያስረክብ የማይገደድ ሆኖ እያለና 1ኛ ተጠሪ ለቆ እንዲያስረክብ ሊገደድ የሚገባው ቀሪውን 554 ካ.ሜ ሆኖ እያለ አጠቃላይ ለ1ኛ ተጠሪ በይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የተሰጠውን 754 ካ.ሜ ያስረክብ እንዲሁም በዚሁ ይዞታ ላይ የተሰጠው ካርታ እንዲሰረዝ መወሰኑ ከተረጋገጠው ፍሬነገር አንጻር ተገቢ ሆኖ ስላላገኘነው 1ኛ ተጠሪ ሊያስረክብ የሚገባው በፍቃድ ከያዘው 200ካ.ሜ ውጭ ያለው ጨምሮ የያዘውን ቀሪው 554 ካ.ሜ ሊሆን ይገባል እንዲሁም ለ1ኛ ተጠሪ በአመልካች ቀድሞ ባለቤት ፈቃድ ከያዘው 200ካ.ሜ ውጪ ያለው የአመልካችን ይዞታ በማስፋፋት ስለመያዙ በተረጋገጠው 554 ካ.ሜ ባካተተ መልኩ የሰጠው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ሊስተካከል ይገባል በማለት በዚህ አግባብ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ሊታረም የሚገባው ሆኖ ስላገኘነው ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 42089 በቀን 14/07/2015 ዓ.ም፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምስራቅ ኦሮሚያ ቋሚ ምድብ ችሎት በመ/ቁ 417334 በቀን 27/7/2015 ዓ.ም፣ እንዲሁም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 422920 በቀን 2/8/2015 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ እና ትዕዛዝ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር *ሥን-ሥርዓት መመሪያ* ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9/1/ለ ተሽሯል፡፡
2. አዳማ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 39819 በቀን 13/06/2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር *ሥነ-ሥርዓት መመሪያ* ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9/1/ለ መሰረት ተሻሽሏል፡
3. 1ኛ ተጠሪ ለአመልካች ለቆ ሊያስረክብ የሚገባው በአመልካች ቀድሞ ባለቤት ፈቃድ ከያዘው 200ካ.ሜ ውጭ ያለውን 554 ካ.ሜ ነው በሚል ተወስኗል፡፡
4. 2ኛ ተጠሪ ለ1ኛ ተጠሪ በካርታ ቁጥር 783/12፤ በቀን 19/10/2012ዓ.ም በ754ካ.ሜ ላይ የሰጠው

<u>ማስታወሻ</u>፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በመሰረዝ በ1ኛ ተጠሪ በይዞታው ላይ መብት ሊፈጠርለት የሚገባው አስቀድሞ በፈቃድ በያዘው 200ካ.ሜ ላይ ብቻ ነው በሚል ተወስኗል፡፡

5.

2ኛ ተጠሪ ለአመልካች በ1095ካ.ሜ ላይ በህግ በተቀመጠው መስፈርት ተከትሎ የባለይዞታነት ማስረጃ እና የግንባታ ፈቃድ እንዲሰጣት ተወስኗል፡፡

6.

የዚህ ችሎት ወጭና ክሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን የቻሉ፡፡

መዝገብ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፍ/ደ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መዝገብ ቁጥር -246494

ቀን -06/02/2017

ዳኞች - ሽመክት አሰፋ

ገበየሁ ፈለቀ

አለማየሁ ሹናራ

ተናኜ ጥላሁን

ዘውዲቱ ታደሰ

አመልካቾች - አቶ መኩሪያው ዘውዴ - አልቀረቡም

ተጠሪ - የፍኖተ ሰላም ከተማ አስተዳደር ከተማ - አልቀረቡም

መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው ለምርመራ ስለሆነ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ጉዳዩ የተጀመረው በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በተጠሪ ላይ ያቀረበው ክስ አመሰራረት ይዘት በአጭሩ ተከሳሽ 0.2536 ሄክታር መሬት ለቤቶች ልማት ማህበር ወስዶ ካሳና ምትክ ቦታ ያልሰጠኝ ስለሆነ ካሳ ብር 294,244.00 (ሁለት መቶ ዘጠና አራት ሺህ ሁለት መቶ አርባ አራት ብር) እና ምትክ ቦታ እንዲሰጠኝ ኪሳራ 90,000.00 ብር (ዘጠና ሺህ ብር) እንዲወሰን የሚል ነው፡፡ የስር ተከሳሽ ለክሱ የሰጠው መልስ ከሳሽ መንግስት ሰራተኛ በመሆኑ ካሳ የማግኘት መብት የለውም፡፡ የካሳ መጠኑ የተጋነነ ነው፡፡ ኪሳራ 90,000.00 መጠየቁ አግባብ አይደለም፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የቤት መስሪያ ቤት (ምትክ) ቦታ ሊሰጥ አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡ ግራ ቀኙ የቃል ክርክርም አሰምተዋል፡፡ የግራ ቀኙ የፅሁፍ እና የቃል ክርክር ከተጠናቀቀ በኃላ ከሳሽ ክስ ለማቅረብ መብትና ጥቅም አለው ወይስ የለውም? ለከሳሽ ካሳ እና ትክ ቦታ ልሰጠው ይገባል አይገባም? የካሳ መጠኑ የተጋነነ ነው ወይስ አይደለም? የሚሉትን ጭብጥ በመያዝ የግራ ቀኙን ማስረጃ ቃል ሰምቷል፡፡ የከሳሽ ምስክር ለከሳሽ 0.5538 ሄክታር መሬት መኖሩን መሬቱን ተከሳሽ ለቤቶች ህብረት ስራ ማህበር ቤት ለመስራት መውሰዱን ለከሳሽ 0.3 ሄክታር መሬት ካሳ መክፈሉን ቀሪ 0.2538 ሄክታር መሬት ካሳ ያልተከፈለ መሆኑን ከሳሽ ቅሬታ አቅርቦ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ተመርጠን አጣርተናል ወደ ከተማ አስተዳደር የገባ የገጠር ቀበሌ መሬት ላይ ይዞታ የነበራቸው የመንግስት ሰራተኛ የነበሩ ግለሰቦች በምርጫ መሬት የመረጡት መንግስት ስራ ለቀው መሬት ያገኙ መሆናቸው ከሳሽ መንግስት ስራ ለቀው መሬት ያገኙ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ከሰው ምስክር በተጨማሪ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ቀርቧል፡፡ የተከሳሽ ምስክሮች በመሬቱ ላይ ከሳሽ መብትና ጥቅም የሌለው መሆኑን አላስረዱም፡፡ የከሳሽ መሬት በተወሰደበት ጊዜ ያለው የካሳ አሰላል አንድ ካሬ ሜትር 38.047 ብር በመሆኑ 0.2538 ካሬ ሜትር ሲባዛ 38.047 ብር 96,563.00 ከ 9% ወለድ ጋር ታስቦ ካሳ ተከሳሽ እንዲከፍል ምትክ ቦታ ተከሳሽ የመስጠት ግዴታ የለበትም ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ላይ ከሳሽ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ቅሬታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 01-56135 በቀን 13/05/2014 ኢ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤትን ፍርድ አፅንቶታል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት ሰበር ቅሬታ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 111574 በቀን 03/06/2015 ኢ.ም በዋለው ችሎት በገጠር መሬት ላይ ያለውን የይዞታ የመጠቀም መብት በተመለከተ የሚቀርበው ክርክር መቅረብ ያለበት በወረዳ ፍርድ ቤት ነው እንጅ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዳልሆነ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር በመዝገብ ቁጥር 217195 ግንቦት 30 ቀን 2014 ኢ.ም ትርጉም የሰጠ ስለሆነ ጉዳዩን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለማየት የስረ ነገር ስልጣን የለውም በማለት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በመሻር አመልካች ክሱን የስረ ነገር ስልጣን ባለው የወረዳ ፍርድ ቤት እንዲያቀርብ ሲል መብቱን ጠብቆ ወስኗል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት ነው፡፡ የአመልካች ሰበር ቅሬታ ይዘቱ በአጭሩ አመልካች በከፊል ባልተወሰነልኝ ጉዳይ ላይ የሰበር ቅሬታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አቅርቦ ሰበር ችሎት ባልተጠየቀ ዳኝነት ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት የስረ ነገር

ስልጣን የለውም በማለት የሰጠው ፍርድ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ ተሽሮ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን አለው ተብሎ ካሳና ትክ ቦታ ተጠሪ እንድሰጥ እንዲወሰን የሚል ነው፡፡

ሰበር ችሎቱ የክልሉ ሰበር ችሎት የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን ሳይኖረው የወሰነ ነው በማለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር በመዝገብ ቁጥር 217195 የሰጠውን ውሳኔ በመጥቀስ የሰበር አቤቱታ ያልቀረበበትን የውሳኔ ክፍል ጭምር በመሻር የመወሰኑ ተገቢነት ለማጣራት ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ በ 08/12/2015 ዓ.ም በተፃፈ መልስ 03 ገፅ አቅርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡ ይዘቱ በአጭሩ አመልካች የመንግስት ሰራተኛ ስለሆነ ካሳ ሊከፈለው አይገባም፡፡ ለአመልካች 0.2538 ሄክታር መሬት መኖሩ ከሚመለከተው አካል ሳይጣራ በደፈናው የተወሰነ ውሳኔ የክልሉ ሰበር በማገናዘብ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 217195 ላይ በሰጠው ውሳኔ መሰረት ጉዳዩ ሊቀርብ የሚገባው ወረዳ ፍርድ ቤት ነው በማለት በገጠር መሬት ጉዳይ በተነሳው ክርክር ከውሰነው ውሳኔ ጋር ተመሳሳይ ነው በማለት ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት የስረ ነገር ስልጣን የለውም ሲል የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ስለሆነ እንዲፀና የሚል ነው፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ በተገለፀው መሰረት የተጠቃለለ በመሆኑ እኛም ከማስቀረቢያ ጭብጥ መሰረት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት የስረ ነገር ስልጣን የለውም በማለት ሽሮ የወሰነበትን አግባብነት እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ መርምረን እንዳተረዳነው ከሆነ አመልካች በተጠሪ ላይ በምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ያቀረበው ክስ 1ኛ የ 0.2538 ካሬ ይዞታ ለህዝብ ጥቅም ተወስዶ ካሳ ያልተከፈለ ስለሆነ ካሳ እንዲከፍል

2ኛ ትክ ቦታ እንዲሰጠኝ የሚል ዳኝነት ጠይቋል አመልካች የጠየቀው የገንዘብ መጠን በድምሩ ብር 384,244.00 ነው፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ የሚገኘው በገጠር ሳይሆን ወደ ከተማ ክልል የገባ የከተማ ይዞታ ነው፡፡ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄም የካሳና ምትክ ቦታ እንዲሰጠኝ የሚል ጥያቄ ነው እንጂ ገጠር እርሻ መሬት እንዲሰጠኝ ጥያቄ አይደለም፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር በመዝገብ ቁጥር 217195 በሆነው መዝገብ ላይ የወሰነው ውሳኔ የሚያስረዳው በካሳ እና ምትክ ቦታ ጥያቄ ላይ ሳይሆን የገጠር እርሻ መሬት ክርክር በሚመለከት ላይ ስለሆነ ከዚህ ጉዳይ ጋር ተመሳሳይነት የለውም፡፡ የአመልካች ጥያቄ ካሳ እና ምትክ ቦታ እንዲሰጠኝ የሚል ስለሆነ የካሳ መጠን በገንዘብ ብር 384,244.00 በመሆኑ በገንዘብ መጠን ከ 300,000.00 ብር በላይ ጉዳይ የማየት ስልጣን ያለው ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንደሆነ የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 223/2007 አንቀፅ 14(2)(ሀ) ስር ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በዚህ አዋጅ መሰረት የስረ ነገር ስልጣን ያለው ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ እንጂ ወረዳ ፍርድ ቤት አይደለም፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ሲጠቃለል የአመልካች ዳኘነት ጥያቄ ለልማት ይዞታው ስለተወሰደ በአዋጅ መሰረት ካሳ እና ምትክ ቦታ ያልተሰጠኝ ስለሆነ ካሳ ብር 294,244.00 እና ለተጉላላሁበት ኪሳራ 90,000.00 ብር በድምሩ ብር 384,244.00 ተጠሪ እንዲከፍል ምትክ ቦታም እንዲሰጠኝ የሚል ስለሆነ ጥያቄው የገጠር እርሻ መሬት እንዲሰጠኝ የሚል ሳይሆን የካሳና ምትክ ቦታ ጥያቄ በመሆኑ በገንዘቡ መጠን ክሱ ሊቀርብ የሚገባው ከ 300,000.00 ብር በላይ በመሆኑ በከፍተኛ ፍርድ ቤት መቅረቡ በአግባቡ ሆኖ እያለ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት የስረ ነገር ስልጣን የለውም ማለቱ አዋጅ ቁጥር 223/2007 ድንጋጌ የሚጣረስ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 2(4)(ለ) እና 10(1)(መ) መሰረት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 111574 በቀን 03/06/2015 አ.ም የሰጠው ፍርድ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስነ ስርአት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9(1)(ለ) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የክርክሩ ገንዘብ መጠን ከሶስት መቶ ሺህ ብር በላይ ስለሆነ የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን አለው ብለናል፡፡
3. የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን አለው ስለተባለ የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ በስረ ነገር ላይ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ አንቀፅ 341(1) መሰረት ለአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መልሰናል፡፡
4. በውሳኔው መሰረት እንዲፈፅም የውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡
5. በዚህ ችሎት የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የራሳቸውን ይቻሉ፡፡
6. በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠ እግድ ካለ ተነስቷል፡፡

## ትዕዛዝ

- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

መ/ዐ　　　　　　　　　　የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መዝገብ ቁጥር - 246518

ቀን - 06/02/2017

ዳኞች - ሸመክት አሰፋ

ገበየሁ ፈለቀ

አለማየሁ ሹናራ

ተናኜ ጥላሁን

ዘውዲቱ ታደሰ

አመልካች - አቶ ቶላ ተፈሪ - ቀረቡ

ተጠሪ - አቶ ግርማ ተፈሪ - ቀረቡ

መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው ለምርመራ ስለሆነ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የተጀመረው በኦሮሚያ ክልል በቄለም ወለጋ ዞን የሰዲ ቃንጫ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የስር ከሳሽ ክስ አቀራረብ ይዘት በአጭሩ በሰዲ ተክሉ ወረዳ ተክሉ ቡሩሪ ቀበሌ ልዩ ቦታው ገቺ በተባለ ስፍራ የሚገኝ የእርሻ ማሳ ላይ 1500 የጫት ተክል በግምት ሁለት ጥማድ በሬ የሚሆነው ጫት ጋር ያለው መሬቴን ተከሳሽ ወደ ማሳው ውስጥ አትገባም በማለት ሁከት የፈጠረ ስለሆነ ሁከት እንዲያቆምልኝ በይዞታዬ እና ንብረቴ የመጠቀም መብት ተከብሮልኝ እንዲወሰን የሚል ነው፡፡ ተከሳሽ ለክሱ የሰጠው መልስ በአጭሩ ይዞታውን በተመለከተ ከአባታችን ጋር ተከራክሮ ለከሳሽ ይዞታው ተወስኖለታል፡፡ ጫት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የግል ንብረት ብሎ የሰጠ ሰው የለም፡፡ ጫቱ የከሳሽ አይደለም፡፡ ከሳሽ የላካቸው ሰዎች በእሾህማ አጥር የተከበበውን ጫት ለመጨፍጨፍ ሲመጡ ጫቱ የከሳሽ አይደለም አትቁረጡ በማለት መከልከሉን ይዞታውን አልከለከልም የከሳሽ የግሉ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ የግራ ቀኙ የፅሁፍና የቃል ክርክር ከተጠናቀቀ በኃላ ፍርድ ቤቱ ተከሳሽ ሁከት ፈጥሯል ወይስ አልፈጠረም? ጫት የተከለው ማን ነው? የሚሉትን ጭብጦች ከያዘ በኃላ የግራ ቀኙን ማስረጃ ሰምቷል፡፡ የከሳሽ ምስክሮች እንደ ከሳሽ ክስ ጭብጥ መሰረት አስረድተዋል፡፡ የተከሳሽ ምስክሮች መካከል 1ኛ እና 2ኛ ምስክሮች ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ የከሳሽ መሆኑን ጫቱም ክርክር የተነሳበት ይዞታ ውስጥ የሚገኝ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ተከሳሽም ይዞታው የከሳሽ እንደሆነ አምኗል፡፡ ጫት የተተከለበት ይዞታ የከሳሽ መሆኑን ጫቱ የሚገኘው ክርክር የተነሳበት ይዞታ ውስጥ መሆኑን የከሳሽ ምስክሮች አስረድተዋል፡፡ ከተከሳሽ ምስክሮች መካከል ግማሾቹ ጫት የተተከለበት ይዞታ የከሳሽ መሆኑን ያስረዱ በመሆናቸው ተከሳሽ የሁከት ድርጊት መፈፀሙ በማስረጃ የተረጋገጠ ስለሆነ ሁከቱ ተወግዶ ተከሳሽ ይዞታውንና የጫት ተክሉን እንዲለቁ ሲል ወስኗል፡፡ የስር ተከሳሽ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ቅሬታ ለቄለም ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ ቄለም ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 31104 በቀን 27/03/2015 ኢ.ም በዋለው ችሎት ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ ከሳሽ ተጠቅሞበት እንደማያውቅ ጫቱም የእናቱ መሆኑን ጫቱ በተከሳሽ እጅ የሚገኝ በመሆኑ የሁከት ክስ ማቅረቡ የህግ ድጋፍ የለውም ስለዚህ የተፈጠረ ሁከት የለም በማለት የወረዳ ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ ከሳሽ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት እና ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ይግባኙን ባለመቀበል ሰርዞታል፡፡

የአሁን ሰበር ቅሬታ የቀረበው ከከፍተኛ እስከ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ በተሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት ነው፡፡ አመልካች የሰበር ቅሬታውን በ 01/09/2015 ኢ.ም በ 04 ገፅ ያቀረበ ሲሆን ይዘቱም በአጭሩ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ የሰበር መዝገብ ቁጥር 186348 ቅፅ 25 እና መዝገብ ቁጥር 38228 ቅፅ 9 አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሚቃረን ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የማስረጃ ምዘና መርህ በመጣስ የተሰማው የማስረጃ ቃል በአግባቡ ሳይመረመር እና ሌላ ተጨማሪ ማስረጃ ሳይሰማ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ ተሽሮ የተፈፀመው ሁከት እንዲቆም ተብሎ እንዲወሰን የሚል ነው፡፡ ሰበር በ 25/07/2016 ኢ.ም በዋለው ችሎት ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ እና ንብረት የተከራካሪዎች እናት ነው በማለት የአመልካችን ክስ ውድቅ ማድረጉ ከማስረጃ ምዘና መርህ አንፃር መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አለመሆኑን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 44804፣ 211615 ላይ በሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም አንፃር ለመመርመር ሲባል ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ የበኩሉን መልስ በ 14/08/2016 ዓ.ም በተፃፈ 03 ገፅ አቅርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡ ፍሬ ነገሩ በአጭሩ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ የጫት ተክል ያለበት የእናታችን ይዞታ ነው፡፡ ይዞታውና ጫቱ የእናታችን በመሆኑ የአመልካችና ተጠሪ የጋራ የውርስ ንብረት ነው፡፡ ወራሾች ሳንከፋፈል በጋራ በእናታችን ስም የሚገኝ ነው፡፡ የአመልካች የግል ይዞታ አይደለም፡፡ አመልካች ከአባታችን ጋር የተከራከረው አሁን ክርክር የተነሳበት ይዞታ አይደለም፡፡ አመልካች እናታችን በህይወት በነበሩበት ጊዜ ጫት ተክያለሁ ብሎ ቢከራከርም ይዞታው የግሉ ስለመሆኑ የሚያስረዳ ማስረጃ የለም፡፡ አመልካች የጠቀሰው የሰበር ውሳኔ ከዚህ ጉዳይ ጋር የሚገናኝ አይደለም፡፡ ክርክር የተነሳበት ይዞታና ጫት ተክል የእናታችን በመሆኑ የውርስ ሀብት ሆኖ ያልተከፋፈልነው የወራሾች የጋራ ሀብት ስለሆነ የአመልካች የግል ይዞታ አይደለም፡፡ ስለዚህ የተፈጠረ ሁከት የለም ተብሎ የአመልካች ቅሬታ ውድቅ እንዲደረግልኝ የሚል ነው፡፡ አመልካች በ 5/9/2016 ዓ.ም በተፃፈ 04 ገፅ የሰበር ቅሬታውን በማጠናከር አቅርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ በተገለፀው መሰረት የተጠቃለለ በመሆኑ ለሰበር ቅሬታ መነሻ የሆነው ፍርድ፣ የግራ ቀኙ ክርክርና ከማስቀረቢያው ጭብጥ አንፃር አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ተጠሪ ሁከት ፈጥሯል ወይስ አልፈጠረም የሚለውን ጭብጥ ለማስረዳት ከቀረቡት ማስረጃ ምዘና መርህ አንፃር መርምረናል፡፡ መርምረን እንደተረዳነው ከሆነ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ የግል ይዞታዬን ተከሳሽ እንዳልጠቀም የከለከለ ስለሆነ ከጫት ጋር ያለው የግል ይዞታዬ ላይ የፈጠረው ሁከትን እንዲያቆም እንዲወሰን የሚል ነው፡፡ ተጠሪ ለክሱ የሰጠው መልስ ይዞታው የከሳሽ እንደሆነ በማመን ጫት የከሳሽ የግሉ አይደለም፡፡ የእናታችን ነው በማለት በከፊል አምኖ ተከራክሯል፡፡ ማስረጃ የመመዘንና የመመርመር ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት የቀረቡት የግራ ቀኙ ምስክሮች ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ የአመልካች መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ተጠሪም ቢሆን ይዞታው የአመልካች መሆኑን አምኗል፡፡ የአመልካች ምስክሮች ለክርክሩ መነሻ የሆነው መሬት የጫት ማሳ ያለበት በመሆኑና ይህንን መሬት ተጠሪ አመልካች እንዳይጠቀም የከለከለ መሆኑን ከማስረዳቱም በላይ የተጠሪ ምስክሮችም እንደ አመልካች ምስክሮች ቃል ጋር ተመሳሳይ በሆነ ሁኔታ አጠናክረዋል፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆነው የጫት መሬት የአመልካች መሆኑ በግራ ቀኙ ማስረጃዎች ከመረጋገጡም ሌላ መሬቱ የአመልካች መሆኑ በተጠሪ ባልተካደበት ሁኔታ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔን በመሻር

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የተፈጠረ ሁከት የለም ማለቱ ከማስረጃ ምዘና መርህ አንፃር መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሟል ብለናል፡፡

ሲጠቃለል ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ የአመልካች መሆኑ በተጠሪ ምስክሮች ቃል ጭምር ከመረጋገጡም ሌላ ተጠሪ መሬቱ የአመልካች መሆኑን አምኖ መልስ ሰጥቶ እያለ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሁከት አልተፈጠረም በማለት የወረዳ ፍርድ ቤትን ውሳኔ መሻሩ የማስረጃ ምዘና መርህን የጣሰ ስለሆነ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 2(4)(ሐ)(ሸ) እና 10(1)(ሐ) መሰረት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. የኦሮሚያ ክልል የቄለም ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 31104 በቀን 27/03/2015 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 425167 በቀን 19/05/2015 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 422151 በቀን 04/07/2015 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስነ ስርአት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9(1)(ለ) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የሰዲ ቃንጫ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 02151 በቀን 11/02/2015 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በአግባቡ ስለሆነ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስነ ስርአት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9(1)(ሀ) መሰረት ፀንቷል፡፡
3. የውሳኔው ግልባጫ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠ እግድ ካለ ተነስቷል፡፡

## ትዕዛዝ

- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የሰ.መ.ቁ246525

ጥቅምት 08 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

ሐብታሙ እርቅይሁን

አመልካች፡- ወ/ሮ ሉባባ ያሲን ቀርቧል

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ሱሌይማን ኡመር - ቀርቧል

2. ወ/ሮ አለምጸሀይ ኡመር - አልቀረቡም

መዝገቡ ለፍርድ የተቀጠረ ነው፡፡ በዚሁ አግባብ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካች ግንቦት 01 ቀን 2015 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 415216 ታሕሳስ 27 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 421279 የካቲት 03 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ጉዳዩ የባልናሚስት የንብረት ክፍፍልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአዳማ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን 1ኛ ተጠሪ አመልካች፤ የአሁን አመልካች ተጠሪ፤ የአሁን 2ኛ ተጠሪ ደግሞ ጣልቃገብ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአመልካች እና የ1ኛ ተጠሪ ጋብቻ በፍቺ መፍረሱን ተከትሎ 1ኛ ተጠሪ ለስር ፍርድ ቤቱ የንብረት ዝርዝር አቤቱታ አቅርበዋል፤ አመልካች መልስ እንዲሰጡ ታዞ ዝርዝር መልስ የሰጡ ሲሆን ከመልሳቸውም ጋር አያይዘው ባቀረቡት መስቀለኛ ክስ በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሎጊያ ከተማ ሎጊዜ ዞን አንድ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 01 ውስጥ የሚገኝ የቤት ቁጥሩ 102 ስፋቱ 390 ካ.ሜ የሆነ በአሁኑ ሰዓት በሕንጻ ግንባታ ላይ ያለ እና የንግድ ቤት እና እየተከራዬ ያለ 9 ክፍል ቤት ያለውን ተጠሪው ድርሻቸውን እንዲያካፍሏቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

1ኛ ተጠሪ በሰጡት መልስ በአመልካች ዳኝነት የተጠየቀበት 390 ካ.ሜ ቤት በውርስ ከእናቴ ከወሮ አረጋሽ ይመር ላይ ከእህቴ ወ/ሮ አለምጸሐይ ኡመር ጋር ወራሽነታችንን አረጋጠን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በቀን 15/12/2011 ተሰጥቶን በኮምቦልቻ ከተማ በውርስ ያገኘነውን መኖሪያ ቤት ሸጠን የገነባነው ስለሆነ የክፍፍል ጥያቄ ሊቀርብበት አይገባም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

2ኛ ተጠሪ ባቀረቡት የጣልቃገብነት ክርክር ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ተመሳሳይ ይዘት ያለው ክርክር በማቅረብ ይህ ቤት ከክርክሩ እንዲወጣላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ 2ኛ ተጠሪ ላቀረቡት የጣልቃገብነት ክርከር 1ኛ ተጠሪ ደግፈው መልስ ሰጥተዋል፡፡

አመልካች በበኩላቸው 2ኛ ተጠሪ ላቀረቡት የጣልቃገብነት ክርክር በሰጡት መልስ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት በ 1995 ዓ.ም ባለቤቴ አሮጌ ቤት ደርሶት ሌላ ጎኑ ያለ መሬት ገዝተን ሕንጻ ገንብተን የያዝነው ሲሆን በተጨማሪም 13 በ 20 ካ.ሜ የሆነ ጨምረን የያዝነው ነው በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የግራቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኋላ አመልካች ንግድ ቤቱን በሚመለከት ያቀረቡት ማስረጃ ከባለቤቴ ጋር የገነባነው ነው በማለት ነገሩኝ በማለት ከመግለጽ ውጪ ሌላ አናውቅም ብለዋል፤ ይዞታው የወራሾች መሆኑን ንግድ ቤቱንም በአሁን ሰዓት ተጠሪዎች ካርታ አውጥተውበት እየተጠቀሙበት ያለ ስለመሆኑ ተጠሪዎች ባቀረቡት ማስረጃ አስረድተዋል፤ የንግድ ቤቱ በውርስ የተገኘ ንብረት ስለሆነ አመልካች በጋብቻ ውስጥ የተፈራ ነው በማለት ያቀረቡት የክፍፍል ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለአዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ አመልካች ይህ ንብረት የውርስ መሆኑን ሳትክድ አሮጌውን ቤት አፍርሰን አከራካሪውን ቤት ገንብተን ማከራየት ጀምረናል ብትልም በማስረጃ አላረጋገጠችም፤ ይሁንና አከራካሪውን የንግድ ፎቅ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ በጋብቻ ውስጥ እያሉ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ከ 2009 ዓ.ም ጀምሮ የተገነባ መሆኑን፤ ይህንኑ ፎቅም 1ኛ ተጠሪ እራሱ ቆሞ ያስገነባው መሆኑን፤ ተጠሪዎች ያገኙት የውርስ ንብረት ተሸጦ በተገኘው ገንዘብ የተገነባ መሆኑን እና ከ 2004 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ቀን 15/12/20011 ድረስ ይህ ንብረት የተጠሪዎች የጋራቸው ተብሎ የባለንብረት ማስረጃ እስከሚሰጥ ድረስ ንብረቱ በ1ኛ ተጠሪ ስም ተመዝግቦ የቆየ ስለመሆኑ ማስረጃዎቹ ያስረዳሉ፤ ሆኖም ተጠሪዎቹ የውርስ ንብረት ሸጠው ይህን ፎቅ ሲገነቡ 1ኛ ተጠሪ የግል ነው ብሎ በክልሉ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 74/2 መሠረት አላረጋጠም፤ ስለሆነም የዚህ ፎቅ ግማሽ የአመልካች እና የ1ኛ ተጠሪ ግማሹ ደግሞ የ2ኛ ተጠሪ ድርሻ ነው ሲል ወስኗል፡፡

1ኛ ተጠሪ በበኩላቸው ይህን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ አከራካሪው ንብረት በተጠሪዎች መካከል የተከፋፈለ ስላልሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1060(1) መሠረት የተጠሪዎች የጋራ ንብረት ነው፤ አከራካሪ የሆነው ፎቅ በ 2009 ዓ.ም የተገነባውን ተጠሪዎች በውርስ ያገኙት በኮምቦልቻ ከተማ ውስጥ የሚገኘውን ቤት በመሸጥ የተገነባ ስለሆነ ለብቻ የውርስ ንብረት ሆኖ ሲተዳደር የቆየ እና የተጠሪዎች የንብረት አካል ነው፤ በኦሮሚያ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 74(2) መሠረት የግል ንብረቴ ነው ተብሎ እንዲጸድቅ የሚፈለገው የግል ንበረቱን በልዋጭ የሚገኝ ንብረት በግዢ የሚገኝ ንብረትን የሚመለከት ነው፤ በእጃችን ባለው ጉዳይ ፎቁ የ1ኛ ተጠሪ የግል ንብረት በልዋጭ ወይም በግዢ የተገኘ ሳይሆን የተጠሪዎችን የጋራ ንብረት በመሸጥ የተገነባ ነው፤ ይህ ንብረት በውርስ ከተገኘበት ጊዜ አንስቶ በባለይዞታነት በተጠሪዎች መካከል ያለ እና እየተዳደረ የነበረ የተጠሪዎች የጋራ ንብረት ነው ሲል በስር በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡

አመልካች በተራቸው ይህን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታቸው ተቀባይነት አላገኘም፡፡

አመልካች ግንቦት 01 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ፦ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው የንግድ ቤት ከአመልካች እና ከ1ኛ ተጠሪ ጋብቻ በፊት የነበረው የመሬት ስፋት 20 ካ.ሜ ብቻ ነው፤ የቤቱም ክፍል ብዛት አንድ ደረጃ ብቻ ነው፤ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ ከተጋባን በኋላ 20 ካ.ሜ የነበረው ስፋት 390 ካ.ሜ ሆኖ ተስፋፍቷል፤ አሮጌው ቤት ሙሉ በሙሉ ፈርሶም አሁን ያለው የንግድ ሕንጻ ተሰርቷል፤ ይህ ንብረት ከተጠሪዎች አውራሽ በተገኘ የውርስ ንብረት የተሰራ ስለመሆኑ ማስረጃ የለም፤ ተጠሪዎች ከእናታቸው ያገኙትን የውርስ ቤት ሸጠው ይህንን ሕንጻ መስራታቸውን የሚያሳይ አስቀድሞ የተሰጠ የፍርድ ቤት ውሳኔ የላቸውም፤ 2ኛ ተጠሪም በዚህ ቤት ላይ ምንም መብት የላትም፤ ስለሆነም ይህ ሕንጻ የጋራ መባል ሲገባው ከተጠሪዎች እናት በውርስ የተገኘ ስለሆነ አመልካች የሚስትነት ድርሻ የላትም በማለት የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አከራከሪ የሆነው በአፋር ክልል በሎጊያ ከተማ ቦሎጊያ ክፍለ-ከተማ የሚገኝ ፎቅ ቤት የተጠሪዎችን ንብረት በመሸጥ የተገነባ ነው በሚል የተሰጠው ውሳኔ አግባብነቱ ሊመረመር የሚገባ ሆኖ ስለተገኘ ተጠሪዎች ቀርበው መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

1ኛ ተጠሪ በቀን 13/07/2016 ዓ.ም በሰጡት መልስ፡- አመልካች ከዚህ በፊት በዚህ ፍርድ ቤት በሰ.መ.ቁ 246524 ላይ ተመሳሳይ አቤቱታ አቅርባ በቀን 16/10/2015 ዓ.ም ውድቅ የተደረገባት በመሆኑ በድጋሚ ያስከፈተችው ይህ መዝገብ ውድቅ ሊደረግ ይገባል፤ የተጠሪዎች ክርክር አከራከሪው ሕንጻ የውርስ ንብረት ተሸጦ የተገዛ ሳይሆን ሕንጻው ራሱ የተሰራበት ይዞታ የውርስ ንብረት የሆነ ቤት ያለበት እና በወራሾች መካከል ያልተከፋፈለ ንብረት ነበር የሚል ነው፤ አከራከሪው ሕንጻ የተገነባው በውርስ ይዞታ በሆነ በ 390 ካ.ሜ ላይ በመሆኑ እና ንብረቱንም በግዢ የተገኘ ሳይሆን ቀድሞውንም ያልተከፋፈል የውርስ ንብረት ስለሆነ የክልሉ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 74(2) ተፈጻሚነት የለውም፤ የአመልካች የሰበር አቤቱታ የአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4) እና 10(1) ላይ የተመለከቱትን መስፈርቶች አያሟላም፤ ተጠሪዎች ከእናታችን በውርስ ያገኘነው ንብረት ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት እና ሌላ በኮምቦልቻ ከተማ የሚገኝ ቤት ነው፤ ተጠሪዎች ሁለቱንም ንብረት በስማችን አዛውረናል የኮምቦልቻውን ቤት በመሸጥ አከራከሪ የሆነውን ቤት በፊት የነበረውን ግንባታ በማፍረስ የአሁኑን ግንባታ የገነባን ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፤ ተጠሪዎች በውርስ ያገኘነው ስለሆነ አመልካች ከንብረቱ ላይ ድርሻ አለኝ ብላ ልትከራከር አትችልም፤ አከራካሪው ንብረት የባልና ሚስት ንብረት ሳይሆን ተጠሪዎች በ 1995 ዓ.ም በውርስ ከእናታችን አግኝተን ስመ ሀብቱንም ወደ ራሳችን አዙረን የምንጠቀምበት ነው፤ የውርስ ንብረት ሆኖ በወራሾች መካከል ክፍፍል ያልተደረገበት እና በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1060(1) ላይ በተገለጸው አግባብ በአንድ ላይ የሚተዳደር ነው፤ በውርስ ወይም በስጦታ የተገኘ ንብረት የግል ሆኖ እንደሚቀጥል በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 73 ላይ ተደንግጓል፤ የይዞታውን ስፋት በሚመለከት አመልካች ያነሳችው ክርክር በስር ፍርድ ቤት ያልተነሳ አዲስ ክርክር ነው፤ ስለሆነም የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ተደርጎ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

2ኛ ተጠሪ በቀን 13/07/2016 ዓ.ም በሰጡት መልስ የንብረቱን አመጣጥ በሚመለከት 1ኛ ተጠሪ ከሰጡት መልስ ጋር ተመሳሳይ ይዘት ያለው መልስ ያቀረቡ በመሆኑ ድጋሚ መመዝገብ አላስፈለገም፡፡

አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸውን ይመስላል፡፡ ይህ ችሎትም ያስቀርባል ሲባል የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በቅድሚያ 1ኛ ተጠሪ አመልካች ከዚህ በፊት የሰ.መ.ቁ 246524 የሆነውን መዝገብ አስከፍተው በተዘጋባቸው ሁኔታ አሁን ድጋሚ መዝገብ ማስከፈታቸው አግባብ አይደለም በማለት የተከራከሩ በመሆኑ ይህ ችሎት ተጠቃሹን መዝገብ አስቀርቦ እንደተመለከተው አመልካች ይግባኝ ባይ ሆነው በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 415510 ሕዳር 29 ቀን 2015 ዓ.ም የተሰጠውን ወሳኔ እና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 421278 የካቲት 03 ቀን 2015 ዓ.ም የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም የተከፈተ ነው፤ በእጃችን ባለው መዝግብ ደግሞ አመልካች አቤቱታ ያቀረቡት 1ኛ ተጠሪ ይግባኝ ባይ ሆነው በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 415216 ታሕሳስ 27 ቀን 2015 ዓ.ም አከራካሪውን የንግድ ቤት በሚመለከት የሰጠውን ውሳኔ እና ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 421279 የካቲት 03 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ በመሆኑ በሁለቱም መዝገቦች የተያዘው ጉዳይ የተለያየ ስለሆነ የአመልካች የሰበር አቤቱታ በድጋሚ የተከፈተ ነው በሚል 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡት ክርክር አግባብ አይደለም፡፡

ዋናውን ጉዳይ በሚመለከት አከራካሪ የሆነው የንግድ ቤት አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ በጋብቻ ውስጥ እያሉ ከ 2009 ዓ.ም ጀምሮ የተገነባ መሆኑን፤ ተጠሪዎች ያገኙት የውርስ ንብረት ተሽጦ በተገኘው ገንዘብ የተገነባ መሆኑን ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ የስር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶችን በዚህ ረገድ የለያያቸው ነገር ቢኖር የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪዎቹ የውርስ ንብረት ሸጠው አከራካሪውን የንግድ ቤት ሲገነቡ 1ኛ ተጠሪ የግሌ ነው ብሎ በክልሉ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 74/2 መሠረት ስላላስገለለ የአከራካሪው ፎቅ ቤት ግማሽ የአመልካች እና የ1ኛ ተጠረ ግማሹ ደግሞ የ2ኛ ተጠሪ ድርሻ ነው ከሚል መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡ በአንጻሩ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ደግሞ አከራካሪ የሆነው ፎቅ በ 2009 ዓ.ም የተገነባውን ተጠሪዎች በውርስ ያገኙት በኮምቦልቻ ከተማ ውስጥ የሚገኘውን ቤት በመሸጥ የተገነባ ስለሆነ ለብቻ የውርስ ንብረት ሆኖ ሲተዳደር የቆየ ነው፤ በኦሮሚያ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 74(2) መሠረት የግል ንብረቴ ነው ተብሎ እንዲገለል የሚፈለገው የግል ንብረቱን በልዋጭ ወይም በግዢ የሚገኝን ንብረት የሚመለከት ነው፤ አከራካሪው ቤት የ1ኛ ተጠሪ የግል ንብረት በልዋጭ ወይም በግዢ የተገኘ ሳይሆን የተጠሪዎችን የጋራ ንብረት በመሸጥ የተገነባ በመሆኑ የተጠሪዎች የጋራ ንብረት ነው ከሚል መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡ ስለሆነም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚፈልገው የክርክር መሠረታዊ ጭብጥ በውርስ በተገኘ ይዞታ ላይ ሌላ በውርስ የተገኘን ቤት በመሸጥ በጋብቻ ውስጥ የተገነባ ግንባታ መኖሩ ከተረጋገጠ የኦሮሚያ ክልል የቤተሰብ ሕግ አንጽ 74(2) ለዚህ ጉዳይ ተፈጻሚነት አለው? ወይስ የለውም? የሚለው ነው፡፡

በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 69/1995 እና 83/1996 አንቀጽ 73 እና 78 (1) እና (2) ድንጋጌዎች ባልና ሚስት ጋብቻቸውን በሚፈጽሙበት ጊዜ በየግል የነበሯቸው

ንብረቶች ወይም ከጋብቻ በኃላ በውርስ ወይም በስጦታ በየግላቸው ያገኟቸው ንብረቶች የግል ንብረቶቻቸው ሆነው እንደሚቀሩ፣በአንፃሩ ግን ከግል ጥረታቸውና ከግል ወይም ከጋራ ንብረታቸው የሚያገኟቸው ገቢዎችና ውጤቶች ሁሉ የጋራ ሀብቶቻቸው እንደሚሆኑ ይደነግጋል፡፡ የዚሁ ሕግ አንቀጽ 74(2) ባልና ሚስቱ ከተጋቡ በኃላ አንዱ የግል ሀብቱ በሆነ ንብረት ለውጥ ያገኘው ወይም በግል ገንዘቡ የገዛቸው ወይም የግል ንብረቱን ሸጦ የሚያገኘው ገንዘብ የግል ሀብቱ ሊሆን የሚችለው በዚህ ሁኔታ በግብይት የተገኘው ንብረት የግል ይባልልኝ ብሎ አንደኛው ወገን ጥያቄ ሲያቀርብ እና ፍርድ ቤቱ ሲያጸድቀው ብቻ እንደሆነ ይደነግጋል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በሰ.መ.ቁ 156783 በሰጠው ውሳኔ አስቀድሞ በውርስ የተገኘ ቤት ፈርሶ በምትኩ አዲስ የተሰራው ቤት የአንደኛው ወገን የግል ሐብት ነው ሊባል የሚችለው በክልሉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 69/1995 እና 83/1996 አንቀጽ 74 (2) ስር በተመለከተው መሰረት በምትክ የተሰራው ቤት የተገለለ ከሆነ ብቻ ነው በሚል በየትኛውም እርከን ላይ ለሚገኙ ፍርድ ቤቶች አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

በያዝነው ጉዳይ አከራከሪ የሆነው የንግድ ፎቅ ቤት አከራካሪ የሆነው የንግድ ቤት አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ በጋብቻ ውስጥ እያሉ ተጠሪዎች ያገኙት የውርስ ንብረት ተሸጦ በተገኘው ገንዘብ የተገነባ መሆኑን እና 1ኛ ተጠሪ ይህን በክልሉ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 74(2) መሠረት ይህ ቤት በውርስ ያገኘሁትን ሌላ ቤት ሸጬ በተገኘ ገንዘብ የተሰራ ነው ብለው ያላስገለሉ መሆኑን ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡

1ኛ ተጠሪ እንደሚከራከሩት ከዚህ ቤት ላይ አመልካች ድርሻ ሊኖራቸው አይገባም ሊባል ይችል የነበረው በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በአዋጅ ቁጥር 69/1995 እና 83/1996 በወጣው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 74 (2) ስር በተመለከተው መሰረት ይህንኑ የተሰራውን የንግድ ፎቅ ቤት አስገልለው ቢሆን ኖሮ ነው፡፡ በዚህ ረገድ በ1ኛ ተጠሪ በኩል የቀረበ ክርክር ደግሞ የለም፡፡ ይልቁንም በማስረጃ የተረጋገጠው አከራካሪው የንግድ ፎቅ ቤት ያረፈበት ቦታ የውርስ ቢሆንም ሕንጻው የተገነባው አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ በጋብቻ ውስጥ እንዳሉ መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪዎች በውርስ ያገኙት ኮምቦልቻ ከተማ ውስጥ የነበረው ቤት ተሸጦ የተገኘው ገቢ አከራከሪ የሆነው የንግድ ቤት ከተገነባ 1ኛ ተጠሪ በሕጉ በተመለከተው አግባብ የግላቸው ስለመሆኑ ካላስገለሉ በቀር የግላቸው ነው ተብሎ ሊለይ እንደማይችል እና የአመልካች እና የ1ኛ ተጠሪ የተቀላቀለ ሐብት እንዳለበት የሚያሳይ በመሆኑ በክልሉ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 78 (1) እና (2) ድንጋጌዎች መሰረት የዚህ ቤት ግማሽ በጋብቻ ውስጥ እንደተፈራ ንብረት ይቆጠራል፤ ስለሆነም አከራከሪ የሆነው የንግድ ፎቅ ቤት ግማሹ የአመልካች እና የ1ኛ ተጠሪ የጋራ ሐብት ግማሹ ደግሞ የ2ኛ ተጠሪ የግል ሐብት ነው፡፡ ስለሆነም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህንኑ መሠረት በማድረግ የሰጠው ውሳኔ ተገቢ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ሆኖ ሳለ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ፎቁ አከራካሪው ፎቅ ቤት የ1ኛ ተጠሪን የግል ንብረት በልዋጭ ወይም  በግዥ የተገኘ ሳይሆን የተጠሪዎችን የጋራ ንብረት በመሸጥ የተገነባ በመሆኑ 1ኛ ተጠሪ በክልሉ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 74(2) መሠረት ማስገለል አይጠበቅበትም በማለት የሰጠው ውሳኔ ሕግን አላግባብ በመተርጎም የተሰጠ እና ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም ድንጋጌዊን አስመልክቶ ከዚህ በፊት የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሚቃረን እና መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ውሳኔ**

1. በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 415216 ታሕሳስ 27 ቀን 2015 ዓ.ም አከራካሪውን የንግድ ቤት በሚመለከት የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 421279 የካቲት 03 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 9/1(ለ) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 40410 ጥቅምት 16 ቀን 2015 ዓ.ም አከራካሪውን የንግድ ቤት በሚመለከት የሰጠው ውሳኔ ጸንቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
   - መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የሰበር መዝገብ ቁጥር 246774

ጥቅምት 7 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች፡-----ሽመክት አሰፋ

ገበየሁ ፈለቀ

አለማየሁ ሹናራ

ተናኜ ጥላሁን

ዘዉዲቱ ታደሰ

አመልካች፡----ወ/ሪት ሰርካለም በቀለ አልቀረቡም

ተጠሪ፡---- የአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 12 ቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጠ

**ፍርድ**

ለፍርዱ መነሻ የሆነው ክርክር የባለቤትነት መፋለምን መሰረት ያደረገ በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተጀመረ ሲሆን አመልካች 1ኛ ከሳሽ ሲሆኑ ተጠሪ ተከሳሽ ነበሩ፡፡አመልካች በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ በአጭሩ፡-የአመልካች እና የስር 2ኛ ከሳሽ አባት የሆኑት ሟች ፶ አለቃ በቀለ በየነ በአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 12 ውስጥ 85 ካ.ሜ ስፋት ያለው የቤት ቁጥር 297 በ3ኛ ወገኖች መካከል በነበረ ክርክር በፍ/ቤት ሐራጅ ወጥቶ በመግዛት ከ1971 ዓ/ም ጀምሮ ይዞ የቆየ ሲሆን በ1979 ዓ/ም በቤቱ ዉስጥ አሰጠተግተን ከነበሩ ሰዉ ጋር ተጠሪ ተመሳጥሮ የቤት ቁጥር 297 ን ለሁለት በመክፈል የቤት ቁጥር 297 እና 298 በማድረግ

መብት ሳይኖረዉ የቤት ቁጥር 298 ከ1979 ዓ.ም ጀምሮ ይዞ ስለሚገኝ ተጠሪ የቤት ቁጥር 298 ን ለቆ እንዲያስረክበኝ ሲሉ ጠይቋል ።

ተጠሪ በበኩሉ የቤት ቁጥር 298 ን መንግስት በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት ወርሶ ለረጅም ጊዜ ሲያስተዳድረው የነበረ ሲሆን ይህ ከሆነ ደግሞ የእኔ ነው የሚል አካል በአዋጁ መሰረት የተፈቀደለት ስለመሆኑ ወይንም ለሚመለከተው አካል አመልክቶ ባለመብት ስለመሆኑ ያስወሰነ ካልሆነ በስተቀር መብት እና ጥቅም የለውም በማለት የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ

ችሎት በመ/ቁ 45161 ቅጽ 10 ላይ ትርጉም የሰጠ ሲሆን አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡት ማስረጃ ስለሌለ መብት እና ጥቅም የለውም እንዲባልልን ብለዋል፡፡

የፍ/ቤቱም አመልካች ክሱን ለማቅረብ የሚያስችል መብት እና ጥቅም አላቸው ወይ? የሚል ጭብጥ ይዞ በሰ/መ/ቁ 45161 በመጥቀስ በመንግስት እጅ ለረጅም ጊዜ የቆዩ ቤቶችን በሚመለከት ይገባኛል የሚል ወገን የተፈቀደለት ስለመሆኑ ወይንም ያለአግባብ የተወረሰ ስለመሆኑ ተረጋግጦ የተሰጠ ውሳኔ ከሚመለከተው አካል ማቅረብ ግዴታ የሚጥል ስለሆነ አመልካች ደግሞ ካቀረበችው ማስረጃም ሆነ ፍ/ቤቱ የቤቱን ማህደር አስቀቦ እንደመረመረዉ በማህደር ዉስጥ ይህን የሚገልፅ ማስረጃ ስለሌለ አመልካች ክሱን ለማቅረብ መብት እና ጥቅም የላቸውም ሲል ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በውሳኔው ቅር በመሰኘት ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ ያቀረቡና ዉድቅ የተደረገባቸዉ ሲሆን ቀጥሎም ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ቢያቀርቡም አያስቀርብም ሲል ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡

ይህ ሰበር አቤቱታ የቀረበው አመልካች በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ እንዲታረም በማለት ሲሆን የቀረበው የሰበር አቤቱታም የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ሆነ የተጠሪ ክርክር መሰረት ያደረገው የሰበር ትርጉም ከአዋጅ ውጪ ቤት ተወርሶብኛል ለሚል ሲሆን አከራካሪው ቤት አዋጁ ከወጣ በኂላ በአዋጁ በተፈቀደ እና በፍ/ቤት በወጣ ጨረታ እና ውል የተገዛ እና በደርግ ዘመነ መንግስት ውሉ ተመዝግቦ ማህተም የተደረገበት እና አመልካች ከአዋጅ በኂላ በጨረታ ግዢ መፈጸሙን የሚያስረዳ በቂ ማስረጃ እያለኝ ይህም በቤቱ ላይ መብትና ጥቅም ያለኝ ስለመሆኑ እያሳየ ሳለ የስር ፍርድ ቤት አመልካች በቤት ቁጥር 298 ላይ መብት እና ጥቅም የለሽም መባሉ የሕግ ስህተት ስለሆነ የስር ፍርድ ቤቶች የፈጸሙት የህግ ስህተት እንዲታረም ሲሉ ጠይቋል፡፡

አመልካች ያቀረቡትን የሰበር ቅሬታ መነሻ ተደርጎ ያስቀርባል በመባሉ ምክንያት በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2/4/ሀ እና ሸ/ እና 10/1/ረ/ እንዲሁም በሰበር ስነ ስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 7/3/ ስር በተደነገገው መሰረት ተጠሪ መልሳቸውን እንዲያቀርቡ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ ባቀረቡት መልስም የአዲስ አበባ ከተማ ቤቶች አስተዳደር ቤቶች መመሪያ ቁጥር 140/2015 አንቀጽ 8/12/ ላይ በአዋጅ ቁጥር 47/67 ተወርሰው ነገር ግን መረጃ የጠፋባቸው

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ቤቶች ለአንድም ጊዜ ቢሆን በመንግስት ቤትነት ኪራይ ከተከፈለ በመንግስት ቤትነት ይቀጥላል በማለት መደንገጉ እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመንግስት እጅ ለረጅም ጊዜ የቆዩ ቤቶች ላይ መብት አለን የሚሉ ወገኖች የተፈቀደላቸው ወይንም ከሚመለከተው አካል ባለመብት ስለመሆናቸው አስወስነው ካልቀረቡ መብት እና ጥቅም የላቸውም በሚለው መሰረት አመልካች ቤቱ በመንግስት እጅ ለረጅም ጊዜ የቆየ ስለመሆኑ ባልካዱበት ሁኔታ እና አመልካች ተገዛ የሚሉት ቤት የቤት ቁጥር 297 እንጂ የቤት ቁጥር

298 ባለመሆኑ የቤት ቁጥር 298 ከአዋጅ ቁጥር 47/67 በኂላ በአመልካች ተይዞ የማያውቅ እና መንግስት በተለያየ ጊዜ እያከራየ ይዞ ያለ ቤት በመሆኑ ከዚህ አንጻር አመልካቾ በቤቱ ላይ መብትና ጥቅም የለሽም ተብሎ በስር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ ስህተት የሌለበት በመሆኑ ሊጸና ይገባል ሲሉ መልስ ሰጥቷል።

ይህ ፍርድ ቤት ያስቀርባል ሲባል የተያዘዉን ጭብጥ ከግምት ዉስጥ በማስገባት አመልካች በቤት ቁጥር 298 ላይ ክስ የማቅረብ መብት እና ጥቅም አላት ወይስ የላትም ?የሚለዉን መሰረት በማድረግ ጉዳዩን ከሕጉ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ ተመርምሯል።

እኛም መዝገቡን መርምረን እንዳየነዉ የክሱ መነሻ የሆነዉን የቤት ቁጥር 298 በተመለከተ አመልካች አዉራሽ አባታቸዉ ከአዋጅ ቁጥር 47/67 ወዲህ የቤት ቁጥር 297 ን በጨረታ አሸንፈዉ የገዙትን በሁለት በመክፈል የቤት ቁጥር 297 እና 298 በማሰጠት የቤት ቁጥር 298ን የሆነዉን ተጠሪ ከ1979 ዓ.ም ጀምሮ የያዘብኝ ስለሆነ እንዲመልስልኝ የሚል ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ ይህ የቤት ቁጥር 298 በአዋጅ ቁጥር 47/67 ተወርሶ በመንግስት እጅ ስር ለረጅም ጊዜ የቆየ በመሆኑ ይህ ቤት እንዲመለስላችቀዉ አመልካች ከሚመለከተዉ አካል ያላስወሰኑና የተፈቀደላቸዉ ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ ስለሌለ መብትና ጥቅም የላቸዉም ሲል የመጀመሪያ መቃወሚያ አቅርቦ በዚሁ መቃወሚያ መሰረት በክሱ ላይ አመልካች መብትና ጥቅም የላቸዉም ተብሎ ዉድቅ የተደረገ ሲሆን የዚህን ዉሳኔ አግባብነት ከተያዘዉ ጭብጥ አንፃር ስናየዉ አመልካች በክሳም ያልካደቸዉ ቤቱ ከ1979 ዓ.ም ጀምሮ በመንግስት እጅ የነበረ ስለመሆኑ ነዉ። በመንግስት እጅ ለረጅም ጊዜ የነበሩ ቤቶች በተመለከተ ደግሞ ቤቱ ከአዋጅ 47/67 ዉጪ ተወስዶብኛል የሚል ሰዉ ቤቱ የተፈቀደለት ከሆነ በፕራይቬታያይዜሽን ኤጀንሲ ቤቱ እንዲመለስለት ካለተፈቀደ በስተቀር ለረጅም ጊዜ በመንግስት ቁጥጥር ስር ሆኖ ሲተዳደር የነበረን ቤት በተመለከተ ቤቱ የመንግስት ሆነዉ እንደሚቆጠሩ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የፌደሬሽን ምክር ቤት 6ኛ የፓርላማ ዘመን 3ኛ ዓመት 1ኛ መደበኛ ስብሰባ በመዝገብ ቁጥር 106/15 ላይ በቀን 29/1/2016 ዓ.ም በሰጠዉ የሕገ መንግስት ትርጉም ላይ የተገለፀ በመሆኑ አሁን በእጃችን ባለዉ ጉዳይ የክሱ መነሻ የሆነዉ ቤት ከ 30 አመታት በላይ በመንግስት ቁጥጥር ስር የነበረን ቤት አመልካች ከሚመለከተዉ አካል ቤቱ እንዲመለስላቸዉ የተፈቀደ ስለመሆኑ ያቀረቡት ማስረጃ በሌለበት ሁኔታ ቤቱ በመንግስት እጅ ከ30 አመታት በላይ ከተያዘ በኃላ ይመለስልኝ ሲሉ ያቀረቡት ጥያቄ ከላይ በተጠቀሰዉ የፌደሬሽን ምክር ቤት የሕገ መንግስት ትርጉም አኳያ ተቀባይነት ሌለዉ እና ቤቱም የመንግስት ቤት ሆኖ እንደሚቆጠር የተወሰነ በመሆኑ በዚሁ መሰረት አመልካች በቤቱ ላይ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ያቀረቡት ክስ በተመለከተ በመብትና ጥቅም የለሽም በመባሉ በአግባቡ ስለሆነ ከዚህ አኳያ በስር ፍርድ ቤት በተሰጠዉ ዉሳኔ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አልተገኘበትም ተብሎ ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል።

**ዉሳኔ**

1/የአዲስ አበባ ከተማ የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 052055 ላይ በቀን 12/1/2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የተሰጠዉ ዉሳኔ፣ የአዲስ አበባ ከተማ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 38257 ላይ በቀን 6/3/2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ፣የአዲስ አበባ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 39843 ላይ በቀን 13/6/1015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ ላይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈፀመበት በመሆኑ በፌ/ጠ/ፍ/ቤት የሰበር ስነ -ስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1)(ሀ) መሰረት ፀንቷል።

2/ ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ወገኖች ይቻቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፍ/ደ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የሰ.መ.ቁ.246780

ጥቅምት 06 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች፡......1. ብርሃኑ አመነዉ

2. በእዉቀት በላይ

3. ቀነዓ ቂጣታ

4. ብርሃኑ መንግስቱ

5. ማርታ ተካ

አመልካች፡ ........1. አቶ ፍቃዱ መላኩ
2. ወ/ሮ መዓዛ ተስፋ } ጠበቃ ሙሉጌታ ዘመነ ቀረቡ

ተጠሪ፡.............አቶ ንጉሴ ኡርጋ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

**ፍርድ**

ይህ የቤት ክርክር የተጀመረዉ በኦሮሚያ ክልል በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካቾች የሥር ከሳሾች፣ የአሁን ተጠሪ የሥር ተከሳሽ ሆኖ ሲከራከሩ ነበር። ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ አመልካቾች የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.412233 በ27/06/2015 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ።

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ የአሁን አመልካቾች በሥር ፍ/ቤት ባቀረቡት የክስ አቤቱታ፡ በሱሉልታ ከተማ 01 ቀበሌ ልዩ ቦታ ኖኖ ኖክ የሚባ ቦታ አዋሳኝ በመጥቀስ በካርታ ቁጥር Sul/1730/98 በ1ኛ ከሳሽ (በአቶ ፍቃዱ መላሉ) ስም ተመዝግቦ የሚገኘዉን ቤት በ22/5/2012 ዓ.ም በተደረገ ዉል ለ2ኛ ከሳሽ (ወ/ሮ መዓዛ ተስፋ)

የተሸጠዉን 2ኛ ከሳሽም ቤቱን ተረክቤ አድሼዉ ጠባቂ አድርጌበት እየስተዳደርኩት እያለሁ ተከሳሽ መብት ሳይኖራዉ በ16/8/2012 ዓ.ም ቁልፍ ሰብሮ የያዘብኝ ስለሆነ ለከተማዉ መሬት አስዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት አመልክቼ ካስለቀቁ በኋላ ለሌላ ቦታ የተሰጠዉን ካርታ በማምጣት መስከረም ወር 2014 ዓ.ም ስለያዘብኝ ቤቱን ለቆ ለ2ኛ ከሳሽ እንዲያስረክብ እንዲወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል።

ተከሳሽ በዚህ ክስ ላይ ባቀረቡት ክርክር ከሳሾች ተመሳሳይ መብት ስለሌላቸዉ በአንድነት ክስ ለማቅረብ አይችሉም፤ በከሳሾች መካከል ባለዉ ዉል ሁለቱም ክስ ማቅረብ አይችሉም፤ ክሱን በይርጋ የሚታገድ ነዉ፤ በታዉ የከሳሾች መሆኑን ያቀረቡት ማስረጃ የለም፤ ዉሉም የተመዘገበ ስላልሆነ ዉጤት የለዉም፤ ተከሳሽ በቤት ማህበር ተደራጅቼ በ9/2/1998 ዓ.ም ክፍያ ፈጽሜ በ26/3/1998 ዓ.ም ካርታ ተሰጥቶኝ 25 ቅጠል ቆርቆሮ ሰርቼ ለ16 ዓመታት የሚጠቀምበት ነዉ፤ ቀደም ሲል የሁከት ክስ ቀርቦ 2ኛ ከሳሽ መብት የላትም ተብሎ ክሱ ዉድቅ ሆኗል፤ በተከሳሽ ላይ የተፈጠረዉ ሁከት እንዲቆምልኝ በተወሰነዉ መሰረት የያዝኩት ነዉ እንጂ ከሕግ አግባብ ዉጭ ቁልፍ ሰብሬ አልያዝኩኝም በማለት ተከራክሯል።

ከዚህ በኋላ የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት በተከሳሽ የተነሳዉን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በተመለከተ ምስክሮችን በመስማት መቃወሚያዉን ዉድቅ በማድረግ፣ በዋናዉ ጉዳይ በሰጠዉ ዉሳኔ ለክርክር መነሻ የሆነዉ ይዞታ ሳይሆን ቤት በመሆኑ፣ ቤቱን የሰራዉ ደግሞ ተከሳሽ መሆኑን የሰዉ ምስክሮችም የሚመለከተዉ አካልም አጣርቶ ባቀረበዉ ማስረጃ ስለተረጋገጠ፣ ከሳሾች ቤቱን ስለመስራታቸዉ ካለመረጋገጡም በላይ እንደክሳቸዉ ተከሳሽ የቤቱን ቁልፍ ሰብሮ መግባቱን በማስረጃ ያላስረዱ በመሆኑ ክስ የማቅረብ መብት የላቸዉም በማለት ክሱን ዉድቅ በማድረግ ወስኗል። የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረበዉን ይግባኝ በትዕዛዝ ዉድቅ በማድረግ የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል። የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ።

የአሁን አመልካቾች ግንቦት 7 ቀን 2015 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ አመልካቾች ይዞታዉ በእኛ ስር የቆየ መሆኑን፣ በ1ኛ አመልካች ስም የተሰጠዉ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የቀረበዉ በመሆኑ፣ ቤቱን የሰራዉን 1ኛ አመልካች መሆኑን፣ ተጠሪ የተመራዉ ቦታ ሌላ ቦታ መሆኑን በሰነድና በሰዉ ምስክሮች አስረድተን እያለ የሥር ፍ/ቤት የመክሰስ መብት የላችሁም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ ስህተት ነዉ፤ የአሁን 1ኛ አመልካች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ያለዉ በመሆኑ በቤቱ ላይ የባለሀብትነት መብት አለዉ፤ ተጠሪ የተመራዉ ቦታም ሆነ የተሰጠዉ ካርታ ከአመልካቾች ቦታ ጀርባ የሚገኝ ነዉ እንጂ ተደርቦ የተሰጠ ቦታ እንኳን አይደለም፤ አመልካቾች ቤቱን መስራታችን በሰዉ ምስክሮች አስረድተን እያለ የሥር ፍ/ቤት ቤቱን የሰራዉ ተጠሪ ነዉ በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲሻርልን ባቀረብነዉ ዳኝነት መሰረት እንዲወሰንልን በማለት አመልክቷል።

ይህ ሰበር ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣የሥር ፍ/ቤት አመልካቾች አከራካሪዉን ቤት በተመለከተ ክስ ለማቅረብ መብትና ጥቅም የላቸዉም ክሳቸዉን ዉድቅ በማድረግ የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ወይስ አይደለም የሚለዉን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.33 (2) እና ይህ ሰበር ችሎት በሰ.መ.ቁ.72980 ላይ ከሰጠዉ አስገዳጅ የህግ ትርጉም አንጻር ለመመርመር ሲባል የሰበር አቤቱታዉ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ባዘዘዉ መሰረት የካቲት 28 ቀን 2016 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል። የመልሱም ይዘት ባጭሩ፡ ተጠሪ ይዞታዉ በ1998 ዓ.ም በከተማዉ መሬት አስተዳደር ተሰጥቶኝ ተረክቤ ቤት ሰርቼ የመንግስት ግብር ከፍዩ ከ16 ዓ.ም በላይ ሲጠቀምበት የቆየሁት ነዉ እንጂ አመልካቾች በክሳቸዉ እንደጠቀሱት ቁልፍ ሰብሬ የያዝኩት አለመሆኑ ተረጋግጦ የአመልካቾች ክስ ዉድቅ መደረጉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሌለዉ በመሆኑ ቅሬታዉ ዉድቅ እንዲደረግልኝ በማለት በዝርዝር ተከራክሯል። አመልካቾች መጋቢት 11 ቀን 2016 ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸዉን በማጠናከር ተከራክሯል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር እና የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆኑትን የሥር ፍ/ቤቶችን ዉሳኔዎች አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል። እንደመረመርነዉ አመልካቾች ባቀረቡት ክርክር አከራካሪዉ ይዞታና ቤት በ1ኛ አመልካች ስም ተመዝግቦ የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ የተሰጠዉ ቤቱን የሰራዉ 1ኛ አመልካች መሆኑን እና በዉል ለ2ኛ አመልካች መተላለፉን ቤቱን ሲያስተዳደሩ እንደነበር እና ተጠሪ የሌላ ቦታ ካርታን በማምጣት እንደያዘባቸዉ ገልጸዉ ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን፣ ተጠሪ በበኩሉ አከራካሪዉን ይዞታ በማህበር ተደረጅቶ በ1998 ዓ.ም ተሰጥቶት ቤቱን ሰርቶ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ወስዶበት ግብር እየገበረ እየተጠቀምበት ያለዉ መሆኑን እንጂ አመልካቾች እንደምሉት እንዳልያዘ ተከራክሯል። ከዚህ አንጻር የሥር ፍ/ቤት የሰዉ ምስክሮችን የሰማ እና የሚመለከተዉ አካል ስለጉዳዩ አጣርቶ እንዲያቀርብ በተሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረት የኮሚቴ ሪፖርት የቀረበ መሆኑን እና ባለሙያ ቀርቦ ማብራሪያ መስጠቱንም መዝገቡ ያሳያል። በዚህ መሰረት ከቀረበዉ ሪፖርትና ከባለሙያዉ ማብራሪያ መረዳት እንደሚቻለዉ ይዞታዉ የ1ኛ አመልካች ካርታን እንደሚያሳይ፣ የተጠሪ ካርታ ከጀርባ ያለዉን ቦታ እንደሚያሳይ፤ ነገር ግን በዳታ ቤዝ ደግሞ ሁለቱም ካርታ አንድ ቦታ እንደሚያሳዩ፤ ቤቱን የሰራዉ ተጠሪ መሆኑን ምስክሮች ያስረዱና ቁልፍ ሰብሮ እንደያዘ አመልካቾች በማስረጃ እንዳላስረዱ የሥር ፍ/ቤት የዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል። ከዚህ መረዳት እንደሚቻለዉ ግራ ቀኛቸዉ በሚመለከተዉ አካል የተሰጠ የባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ወይም ካርታ የተሰጣቸዉ መሆኑን እና እነዚህ ካርታዎች በዳታ ቤዝ ሲታይ አንድ ቦታ እንደሚያሳዩ የተገለጸ በመሆኑ ይህ ምን ያመለክታል፣ እንዲሁም ተጠሪ ቤቱን የሰራቸዉ ከሚመለከተዉ የከተማ አስተዳደር የግንባታ ፈቃድ ተሰጥቶት ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነጥብ መታየቱን የሚያመለክት ነገር የለም።

በዚህ መሰረት ከግራ ቀኛቸዉ ክርክርና ከቀረበዉ ማስረጃ አንጻር እንደጭብጥ ታይዞ አግባብነት ባለዉ ማስረጃ ተጣርተዉ ዉሳኔ ማግኘት የሚገባዉ ጉዳዮች፡

1. የሥር ፍ/ቤት የግራ ቀኛቸዉ ክርክር ቤትን የሚመለከት ቢሆንም ቤት የሚሰራዉ በይዞታ ላይ እንደመሆኑ መጠን፣ አከራካሪዉ ቤት ማን ሰራዉ የሚለዉ ነጥብ መጣራቱ ቢሆንም ከዚህ ጋር ተያዞ ምላሽ ማግኘት ያለበት ጉዳይ ቤቱ የተሰራበትን ይዞታ ከሚመለከተዉ የመንግስት አካል በሕጋዊ መንገድ አግኝቶ የያዘዉ 1ኛ አመልካች ነዉ ወይስ የአሁን ተጠሪ ነዉ? የሚለዉ ነጥብ ሳይጣራ

መታለፉ ተገቢ አይደለም። በመሆኑም አከራካሪዉ ቤት የተሰራበትን ይዞታ 1ኛ አመልካች በምን አግባብና መቼ ከሚመለከተዉ የመሬት አስተዳደር አካል እንደገኘ፤ በሌላ በኩል የአሁን ተጠሪ ደግሞ ካቀረበዉ ክርክር አንጻር ይዞታዉን በማህበር ተደራጅቶ በ1998 ዓ.ም በከተማዉ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት እንደተሰጠዉ የገለጸ በመሆኑ፣ ተጠሪ ይዞታዉን በምን አግባብ እና መቼ እንደገኘ፣ ተጠቃሹ ይዞታ የማህበር ይዞታ የነበረ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚሉት ነጥቦች ከሚመለከተዉ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት እና ከተባለዉ የቤት ማህበር ተጣርቶ መለየት ያለበት ጉዳይ እንዲሁም ፍ/ቤቱም የቤቱን ማህደር አስቀርቦ በመመርመር ተገቢዉን መወሰን ያለበት ጉዳይ ነበር።

2. የሥር ፍ/ቤት ከሰጠዉ ዉሳኔ መገንዘብ እንደሚቻለዉ አከራካሪዉን ቤት የሰራዉ የአሁን ተጠሪ መሆኑን የተገለጸ ቢሆንም ተጠሪ ይህን ቤት የሰራዉ ከሚመለከተዉ የከተማ አስተዳደር ሕጋዊ የግንባታ ፈቃድ በመዉሰድ ነዉ ወይም በምን አግባብ ነዉ የገነባዉ? የሚለዉ ነጥብ ከሚመለከተዉ የከተማዉ አስተዳደር አካል ተጣርቶ ማስረጃ ቀርቦ መታየት ያለበት ጉዳይ ነበር።
3. እንዲሁም ከፍ ሲል እንደተጠቀሰዉ የግራ ቀኛቸዉ ካርታ በዳታ ቤዝ አንድ በታ እንደ የሚያሳዩ መገለጹ እነዚህ ካርታዎች በአንድ ይዞታ ላይ ተደርቦ የተሰጠዉ ናቸዉ ወይስ አይደለም? ካርታዎቹ በአንድ ይዞታ ላይ ተደርቦ የተሰጡ እንደሆነ ከሁለቱ ካርታዎች ቅድሚያ የተሰጠዉ ካርታ የማን ነዉ? ሕጋዊ ዉጤቱስ ምንድን ነዉ? የሚሉት ነጥቦች ከሚመለከተዉ የከተማዉ አስተዳደር አካል ተጣርቶ በሕግ አግባብ ታይቶ መወሰን ያለበት ጉዳይ ነበር።
4. በሌላ በኩል ይህ ጉዳይ ከፍ ሲል በተጠቀሰዉ አግባብ ተጣርቶ በቀረበዉ ፍሬ ነገር አከራካሪዉ ይዞታ የ1ኛ አመልካች ካርታ መሆኑን የሚያሳይ እንደሆነ እና ቤቱን የሰራዉ ግን የአሁን ተጠሪ መሆኑ ከተረጋገጠ ሕጋዊ ዉጤቱ ምንድን ነዉ? የሚለዉ ነጥብ መታየት ያለበት ጉዳይ ነበር።

በመሆኑም በሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ እንደተመለከተዉ 1ኛ አመልካች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ያለዉ እና ቤቱን በዉል ለ2ኛ አመልካች ማስተላለፉ ተመልክቶ እያለ፣ የሥር ፍ/ቤት አመልካቾች ይህን ክስ ለማቅረብ መብትና ጥቅም የላቸዉም በማለት የቀረበዉን ክስ ዉድቅ ማድረጋቸዉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.33 (2) ድንጋጌ የሚቃረን በመሆኑ ተቀባይነት የለዉም ብለናል። እንዲሁም ከፍ ሲል በዝርዝር እንደተመለከተዉ ከግራ ቀኛቸዉ ክርክር እና ከቀረበዉ ማስረጃ አንጻር ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት እንደጭብጥ ተያዘዉ አግባብነት ባለዉ ማስረጃ ተጣርቶ ዉሳኔ ሊሰጥባቸዉ የሚገቡ ጉዳዮች ሳይጣሩ መወሰኑ ይህ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ.72980 እና በሌሎች መዛግብት ላይ ከሰጠዉ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ጋር የሚቃረን በመሆኑ የሕግ ድጋፍ የለዉም። ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቶች የግራ ቀኙን ክርክር በዚህ አግባብ አጣርቶ መወሰን ሲገባቸዉ ይህን ሳያደርጉ የሰጡት ዉሳኔ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.136፣ 264፣ 327 (3)፣ 345 እና 246-249 ድንጋጌዎች ይዘትና ዓላማ የሚቃረን በመሆኑ ተቀባይነት የለዉም ብለናል።

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች የግራ ቀኛቸዉን ክርክር እና የቀረበዉን ማስረጃ መሰረት በማድረግ ከፍ ሲል በተመለከተዉ አግባብ ጭብጥ በመያዝ የግራ ቀኙን ክርክር አጣርተዉ መወሰን ሲገባዉ ይህን ሳያደርጉ የሰጡት ዉሳኔ ባልተጣራ ጉዳይ ዉሳኔ እንደመስጠት የሚያስቆጥርና አስገዳጅ የሰበር ዉሳኔን የሚቃረን በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ብለን ተከታዩን ወስነናል።

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

## ዉሳኔ

1. የፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.44953 በ25/05/2015 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.412233 በ27/06/2015 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9 (1) መሰረት ተሽሯል።
2. የፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍርድ የዘጋዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ በፍርድ ሐተታዉ በተመለከተዉ አግባብ ከፍ ሲል የተጠቀሱትን ጭብጦች ከሚመለከተዉ አካል ተጣርቶ ማስረጃ እንዲቀርብ በማድረግ፣ ተጠሪ ከገለጸዉ የቤት ማህበር ጉዳዩ ተጣርቶ እንዲቀርብ በማድረግ፣ የቤቱን ማህደር በማስቀረብ በመመርመር እንዲሁም አግባብነት ባለዉ ማስረጃ በማጣራት ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ እንዲሰጥበት በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9 (2) መሰረት ተመልሶለታል።
3. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ።
4. ግራ ቀኙ የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ።

**መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ይመለስ።**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፍ/ደ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ዳኞች፡-እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች፡- አቶ ማሙሽ ተሾመ

ተጠሪ፡- የበረኸት ወረዳ ቀበሌ 06 አስተዳደር ጽ/ቤት

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ በዳኞች የእረፍት ጊዜ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

# ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች በ01/09/2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በረኸት ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 09325/15 በቀን 09/05/2015 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 0140232 በቀን 14/06/2015 ዓ.ም እንዲሁም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 0314134 በቀን15/06/2015 ዓ.ም በማጽናት መወሰናቸው መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለታቸው ሲሆን በስር ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ከሳሽ ሆነው ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ሆነው ውርስን በተመለከተ ጉዳይ ተከራክረዋል፡፡

በስር ፍ/ቤት አመልካች በቀን 04/01/2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ አባታቸው አቶ ተሾመ ፍቅሬ ከሞቱ በኋላ ከአያታቸው ከአቶ ፍቅሬ ሃይሌ ጋር ሲኖሩ አያታቸው በመሞታቸው የአያታቸው ወራሽ መሆናቸውን ያረጋገጡ መሆኑን በመግለጽ ተጠሪ ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ በህገ ወጥ መንገድ የያዘውን የአያቴን የእርሻ መሬት ለቆ እንዲያስረክበኝ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪም በቀን 2502/2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረበው መልስ ክሱ ከዚህ በፊት ታይቶ ውሳኔ ያገኘ ነው፣ መሬቱ ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ የተያዘ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ይታገዳል፣ አመልካች ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብትና ጥቅም የለውም የሚል መቃወሚያና በፍሬ ነገር ረገድ ደግሞ የአመልካች አያት በ1987 ዓ.ም

ሽፍታ ተብሎ ምህረት ቢደረግለትም ለምህረቱ እምቢተኛ በመሆኑ በአማራ ክልል መንግስት ትዕዛዝ መሬቱ የተወረሰ በመሆኑ ለአመልካች ሊመለስለት አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም በመጀመሪያ ደረጃ መቃዎሚያው ላይ አከራክሮ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ በዚሁ ጉዳይ በዚሁ ፍ/ቤት በመ.ቁ 03107/07 በከሳሽ አቶ ማሙሽ ተሾመ እና በተከሳሽ አቶ ሃ/መስቀል መንገሻ የበረኸት ወረዳ ቀበሌ 06 ሊቀ መንበር መካከል በተደረገ ክርክር ተከሳሽ የያዙት የከሳሽ መሬት የሌለ በመሆኑ ሊጠየቁ አይገባም ተብሎ የተወሰነ ሲሆን ሟች አቶ ፍቅሬ በህይወት እያሉ የሌላቸውን መብት አመልካች ሊጠይቁ የማይችሉ በመሆኑና በወቅቱ ተከሳሽ የነበረው የአሁን ተጠሪ በመሆኑ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 5 መሰረት ከዚህ ቀደም በፍርድ ያለቀ ነው በማለት ወስኗል፡፡

አመልካችም በዚህ ውሳኔ ቅሬታ አድሮብኛል በማለት በመጀመሪያ ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ አቤቱታ ከዚያም ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቶቹ ጉዳዩን መርምረው የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ስህተት የለበትም በማለት አቤቱታውን ውድቅ አድርገዋል፡፡

አመልካችም የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት በ01/09/2015 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ለዚህ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፦ የስር ፍ/ቤት ለውሳኔው መሰረት ያደረገው ከዚህ ቀደም በመ.ቁ. 01107/07 አቶ ሀይለ መስቀል መንገሻ የተባለው ተከሳሽ በአከራካሪው መሬት ተጠያቂ ሊሆን አይገባም በሚል የተሰጠውን ውሳኔ ሲሆን አሁን የተከሰሰው ግን ቀበሌው ሆኖ እያለና ቀበሌውም አከራካሪውን መሬት የመያዝ አለመያዙ ጉዳይ ላይ ውሳኔ ባልተሰጠበት ሁኔታ የስር ፍ/ቤት ጉዳዩ በፍርድ ያለቀ ነው በማለት መወሰኑና ከዚያ በኋላ ጉዳዩ የቀረበላቸው ፍ/ቤቶች ሳያርሙት ማለፋቸው መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ተሸሮ ጉዳዩ በፍርድ አላለቀም ተብሎ ክርክሩ ይቀጥል ተብሎ እንዲወሰን ስል እጠይቃለው የሚል ነው፡፡

አቤቱታው የቀረበለት የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ለዚህ ችሎት ከመራው በኋላ ይህ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ፦ አመልካች ለዚህ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነውን ክስ ያቀረቡት በቀበሌ አስተዳዳር ጽ/ቤት ላይ መሆኑ፣ ቀደም ሲል በመዝገብ ቁጥር 01107/07 ያቀረቡት ክስ ደግሞ አቶ ሀ/መስቀል መንገሻ በተባሉት ግለሰብ ላይ ከመሆኑ አኳያ ጉዳዩ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው መባሉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5 (1) ከተቀመጡ መስፈርቶች አንጻር የተከራካሪዎች ተመሳሳይነት የሚለውን የሚያሟላ መሆን አለመሆኑ ከህጉና ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 168195 እና ሌሎች በርካታ መዛግብት ከሰጠው አስገዳጅ ትርጉም አኳያ ህጋዊነቱን ለመመርመር ተጠሪ መልስ ይስጡበት ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪም በዚህ ትዕዛዝ መሰረት በ04/08/2016 ዓ.ም የተጻፈ መልስ ያቀረበ ሲሆን ይዘቱም፦ የስር ፍ/ቤት ለውሳኔው መሰረት ያደረገው በመ.ቁ 01107/07 አቶ ሀ/መስቀል መንገሻ በተባሉት የቀበሌው ሊቀመንበር በነበሩት ግለሰብ ላይ የቀረበ ክስ ይምሰል እንጂ ግለሰቡ ቀበሌውን ወክለው የተከራከሩ በመሆኑ፣ የክርክሩ ይዘት ቀበሌውን የሚመለከት በመሆኑ፣ የተጠየቀው ዳኝነትም በተቋማዊ ችሎታ እንጂ በተከሳሹ የግለሰብ ችሎታ ላይ ባለመሆኑ፣ ጭብጡም አሁን ከቀረበው ክስ ጋር ተመሳሳይነት ያለው በመሆኑ እንዲሁም የፍርዱ ይዘትም የአመልካች አያት በህይዎት እያሉ የተወረሰባቸውን መሬት አመልካች አሁን ለመጠየቅ የማይችል መሆኑን የሚገልጽ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5 መሰረት ጉዳዩ በፍርድ ያለቀ ነው መባሉ ተገቢነት ያለው በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ስህተት የለበትም ተብሎ እንዲወሰን እጠይቃለው የሚል ነው፡፡

አመልካችም በ22/08/2016 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ አቤቱታቸውን አጠናክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከትነው ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለበትን ጭብጥ መሰረት በማድረግ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡እንደመረመርነዉ ግራቀኙን ያከራከረዉ ጉዳይ አመልካች በበረኸት ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 09325/15 በተጠሪ ላይ ያቀረቡት የውርስ ሀብት ያስረክበኝ የዳኝነት ጥያቄ የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ ጉዳይ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ ነው፡፡

ክርክሮች በአነስተኛ ወጪና ምክንያታዊ በሆነ አጭር ጊዜ ፍትሐዊ እልባት የሚያገኙበትን የክርክር ሂደት አመራር ስርዓት መዘርጋትን መሰረታዊ አላማው ያደረገው የፍትሐ ብሀር ስነስርዓት ህጋችን ተከራካሪ ወገኖች ለአላስፈላጊ የጊዜና የወጪ ብክነት ሳይዳረጉ ክርክሮች በአንድ ደረጃ መቋጫ እንዲያገኙ የሚያደርግ (finality) ሥነ ሥርዓት መዘርጋት እንዲችሉ ፣ የፍርድ ቤቶች የክርክር አመራር በአነስተኛና ምክንያታዊ በሆነ የጊዜ፣የሰዉ እና የገንዘብ ሀብት አጠቃቀም (judicial economy) ተከናዉኖ ወጥነት ያለዉን (consistent) እልባት እንዲያገኝ ጥብቅ ክትትልን እንዲተገብሩ፣ እንዲሁም ተከራካሪዎች አስቀድሞ ዉሳኔ ባገኘ ጉዳይ ላይ በተደጋጋሚ ክስ በማቅረብ የፍትሐ ብሔር ፍትህ አመራር ሒደቱን ባልተገባ መንገድ እንዳይጠቀሙና ተከሳሾችን ባልተገባ ሁኔታ እንዳያጉላሉ ጥበቃን ማድረግ እንዲያስችላቸው በአንቀፅ 5(1) ላይ በሕግ ሥልጣን የተሠጠው ማናቸውም ፍርድ ቤት ክርክሩን ተቀብሎ የመጨረሻ ፍርድ ከሠጠ በኋላ ቀድሞ በፍርድ የተወሰነው ክርክር ሥረ-ነገርና የተያዘው ጭብጥ አንድ ዓይነት ከሆነ በክርክሩ ላይ የነበሩት ወይም ከተከራካሪዎቹ መብት ያገኙ ሦስተኛ ወገኖች በዚያው ነገር ሁለተኛ ክስ ለማቅረብ የማይችሉ መሆኑን ደንግጓል፡፡

የዚህ ድንጋጌ መሰረታዊ ዓላማ ማንኛዉም በሕግ ሥልጣን የተሰጠዉ ፍርድ ቤት ወይም በሕግ የዳኝነት ስልጣን የተሰጠዉ አካል ክርክሩን ተቀብሎ የመጨረሻ ዉሳኔ የሰጠበት ጉዳይ እና በድጋሚ የቀረበዉ ክስ ጉዳይ ሲነጻጸር ሁለተኛዉ ክስ ቀድሞ በፍርድ ከተወሰነዉ ክርክር ሥረ ነገርና ከተያዘዉ ጭብጥ ጋር አንድ ዓይነት ከሆነና በክርክሩ ላይ የነበሩት ወይም ከተከራካሪዎቹ መብት ያገኙት 3ኛ ወገኖች ተመሳሳይ ከሆኑ በዚያዉ ነገር ላይ ሁለተኛ ክስ ወይም ማናቸዉንም ዓይነት ሌላ ክርክር እንዳይደረግ መከልከል ነዉ፡፡ፍርድ ቤቱ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ጉዳዩ አስቀድሞ በፍርድ አልቋል ለማለት በድንጋጌው በዝርዝር የተመለከቱት አራት መስፈርቶች በአንድነት መሟላታቸውን ማረጋገጥ ይገባዋል፡፡የመጀመሪያው መስፈርት ጉዳዩን በመጀመሪያ ከተመለከተው ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣን ጋር የተያያዘ ሲሆን በአንቀፅ 5(1) በሕግ ሥልጣን የተሠጠው ማናቸውም ፍርድ ቤት በማለት የተመለከተው የህግ ሀረግ አስቀድሞ ጉዳዩ የታየው በሕግ ዳኝነት ለመስጠት ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ወይም ዳኝነት ነክ አካል መሆኑን ማረጋገጥን የሚጠይቅ የህጉ መሰረታዊ መስፈርት መሆኑን ከድንጋጌው አጠቃላይ ይዘት የምንረዳው ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም አስቀድሞ በፍርድ ቤት የተሠጠው የመጨረሻ ፍርድ ነው በሚል ከዚያ በኋላ የቀረበውን ክስ ውድቅ ለማድረግ የተመለከተው መስፈርት ፍርድ ቤቱ ክርክሩን አይቶ ጉዳዩ ላይ የመጨረሻ እልባት ወይም ውጤት የሠጠበት መሆን እንዳለበት የሚያስረዳ መስፈርት ሲሆን ሦስተኛው መስፈርት አስቀድሞ ፍርድ ያረፈበት ጉዳይ ሥረ-ነገሩና ጭብጡ አሁን ከተያዘው ጉዳይ ጋር አንድ ዓይነት መሆን እንዳለበት የሚያመለክተው ነው፡፡ ይህ መስፈርት የስረ ነገር እና ጭብጥን ተመሳሳይነት በአንድ ላይ ያስቀመጠ በመሆኑ የክርክሩ መነሻ ጉዳይ አንድ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ፍርድ ቤቱ በጭብጥነት ይዞ የመረመረው ጉዳይ አሁን በተያዘው ክርክርም በጭብጥነት ተይዞ የሚመረመር መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ ሥረ-ነገሩ ተመሳሳይ ሆኖ ነገር ግን የሚያዘው ወይም የተያዘው ጭብጥ የተለያየ ከሆነ በተያዘው ጭብጥ ላይ የቀደመ ፍርድ ባለመኖሩ ጉዳዩ በፍርድ እንዳለቀ ሳይቆጠር ክርክሩ ቀጥሎ ፍርድ ሊያርፍበት የሚችል ጉዳይ ነው፡፡

በሕጉ ላይ የተቀመጠው አራተኛው መስፈርት የተከራካሪዎች ወይም ከተከራካሪዎች መብት ያገኙ ሦስተኛ ወገኖች ተመሳሳይ መሆን እና በእነርሱ መካከል ያለ ክርክር መሆኑ ነው፡፡ፍርድ ቤት ጉዳዩን የሚመረምረውም ሆነ ፍርድ የሚሠጠው ከተከራካሪዎች መካከል በቀረበው የዳኝነት ጥያቄ ላይ የተሻለ መብት ያለው ማን ነው ከሚለው ነጥብ አኳያ ብቻ ነው፡፡ በጉዳዩ ላይ ያላቸው መብት በፍርድ ቤቱ ሳይመረመር እና የመደመጥ ሆነ የመከላከል መብታቸው ሳይከበር ተከራካሪ ያልሆኑ ወገኖች ላይ ፍርዱ አስገዳጅነት አለው ሊባል አይችልም፡፡ስለሆነም ጉዳያቸው በፍርድ አልቋል ሊባሉ የሚችሉት ተከራካሪ ወገኖች መብታቸው በአግባቡ ተመርምሮ፤የመደመጥና የመከላከል መብታቸው ተጠብቆ በቀደመው ክርክር መሳተፋቸው ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ የተከራካሪዎች ተመሳሳይነት የሚለው ከተከራካሪዎች በሕግ ሆነ በውል

መብት የተላለፈላቸውን ሦስተኛ ወገኖች የመብታቸው ምንጭ የቀድሞው ክርክር ላይ ተከራካሪ በሆኑት ወገኖች ልክ በመሆኑ በእነዚህ ወገኖች ላይም ጉዳዩ አስቀድሞ በፍርድ እንዳለቀ የሚያስቆጥር ነው፡፡ፍርድ ቤቶች ከእነዚህ መስፈርቶች አኳያ አዲስ የቀረበዉን ክስ የተጠቀሱትን የሕጉን መስፈርት ተከትሎ መቅረቡን ማረጋገጥ እና ኋለኛዉ ክስ አስቀድሞ የመጨረሻ ዉሳኔ በተሰጠበት ጉዳይ ላይ የቀረበ መሆኑን ሲያረጋግጡ ኋለኛዉን ክስ ዉድቅ የሚያደርግ (dismissing of the suit) ዉሳኔ የመስጠት ኃላፊነት ይኖርባቸዋል፡፡(በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5፣ 244(2/ለ) እና 245/2 የተመለከተውንና እነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ ይህ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 28522፣ 36780፣243645- እና በሌሎች መዛግብት ላይ የሰጣቸዉን አስገዳጅ የሕግ ትርጉሞች ይመለከቷል)፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይ በስር የበረኸት ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.03107/07 ግንቦት 07 ቀን 2007 ዓም የተሰጠውን ፍርድ እንደተመለከትነው የዳኝነት ስልጣን በተሰጠው ፍርድ ቤት አሁን ከያዝነው ጉዳይ ጋር ተመሳሳይ የስረ-ነገር እና ጭብጥ በሚያስነሳ ጉዳይ ላይ የተሰጠ የመጨረሻ ፍርድ ነው ሊባል የሚችል ቢሆንም ከአራተኛው የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.5(1) መስፈርት አንፃር ስናየው ተመሳሳይ ተከራካሪ ወገኖችን ያልያዘ ሆኖ እያለ በዚህ አግባብም በመ/ቁ.03107/07 ክርክሩ በአመልካችና አቶ ሀ/መስቀል መንገሻ ተካሂዶ ተገቢውን እልባት ያገኘ ጉዳይ ሆኖ ለዚህ የሰበር ቅሬታ መነሻ የሆነው ክርክር ግን በአመልካችና በበረኸት ወረዳ ቀበሌ 06 አስተዳደር ጽ/ቤት የሚደረግ ክርክርን የሚወክል ከተከራካሪ ወገኖች ማንነት አንፃር ፍፁም ተመሳሳይነት የሌለው በመሆኑ፣ይህም አራተኛው የሕጉ ጥብቅ መስፈርት አለመሟላቱን እያሳየ የስር ፍርድ ቤት በዋነኝነትም የተጠሪን መቃወሚያ በመቀበል የአመልካች አቤቱታ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5 መሰረት የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘና በድጋሚ ክስ የቀረበበት ነው በማለት ውድቅ ማድረጉና ይህ ውሳኔ በየደረጃው ባሉት ፍርድ ቤቶች መፅናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ውሳኔ

1. የበረኸት ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 09325/15 በቀን 09/05/2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና ይህንን ውሳኔ በማፅናት የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 0140232 በቀን 14/06/2015 ዓ.ም እንዲሁም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 0314134 በቀን15/06/2015 ዓ.ም የሰጡት ትዕዛዝ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስነስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9(1)(ለ) መሰረት ተሸሯል፡፡

2.አመልካች ያቀረቡት የውርስ ድርሻ ያስረክበኝ ዳኝነት ጥያቄ የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘና በድጋሚ ክስ የቀረበበት አይደለም ብለናል፡፡

3.የስር የበረኸት ወረዳ ፍርድ ቤት በቀሪ የክርክር ነጥቦች ላይ ግራ ቀኙን በማከራከር በህጉ አግባብ የመሰለውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስነስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9(2) መሰረት መልሰንለታል፡፡

4.ግራ ቀኙ በሰበር ክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

**<u>ጉዳዩ ውሳኔ ስላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡</u>**

የሰ/መ/ቁ. 246884

ጥቅምት 05 ቀን 2017 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተፈሪ ገብሩ( ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

ሠናይት አድነው

ሀፊዝ አባጀማል

**አመልካች-**፡- አቶ ዘውገ መአዛ ተ/ማርያም ጠበቃ ገ/እግዚአብሔር ቀረቡ

**ተጠሪዎች-** 1. አቶ ኃ/ገብርኤል ሽፈራው

2. የኢትዩጵያ መድን ድርጅት

3.ወ/ሮ አሰገደች ታደሰ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርዱ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ከውል ውጪ የደረሰ የጉዳት ካሳ ኃላፊነትን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በተጀመረበት የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት 3ኛ ተጠሪ ከሳሽ፣ 1ኛ ተጠሪ ተከሳሽ፤ እንዲሁም 2ኛተጠሪ፣ አመልካች እና አሁን በክርክሩ የሌለ ንብ ኢንሹራንስ እንደ ቅደምተከተላቸው 1ኛ፤2ኛ እና 3ኛ ጣልቃ-ገብ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ 3ኛ ተጠሪ በ1ኛ ተጠሪ ላይ ግንቦት 03 ቀን 2011 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት ክስ ንብረትነቱ የ1ኛ ተጠሪ የሆነው እና የሰሌዳ ቁጥሩ 3-338989 ኦሮ የሆነ የህዝብ ማመላለሻ መኪና የ3ኛ ተጠሪ ልጅ ጎሳ ታደሰ ነሐሴ 8 ቀን 2010 ዓ.ም ከሰንቦ ደብረ ብርሃን እየተጓዘ እያለ በሹፌሩ ጥፋት ምክንያት መስመሩን ለቆ በተቃራኒ አቅጣጫ ሲጓዝ ከነበረው ንብረትነቱ የአመልካች የሆነው ኮድ3-55830 ኢ.ቲ ሲኖትራክ የጭነት መኪና ጋር በመጋጨቱ ልጄ ወዲያውኑ ሞቷል፡፡ ስለሆነም በ1ኛ ተጠሪ መኪና ግጭት ምክንያት ያወጣሁት ወጪና ወደ ፊት የማጣውን ጥቅም በአጠቃላይ ብር 333,000.00 (ሶስት መቶ ሰላሳ ሶስት ሺ.ህ) እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

1ኛ ተጠሪ በሰጠዉ መልስ አደጋው የተፈጠረው የአመልካች መኪና በሚሽከረከርበት ወቅት በመስመሩ ፊት ለፊት እንጨት ተጋድሞ ስለነበር እንጨቱን ለመሸሽ ሲል በ1ኛ ተጠሪ መኪና መስመር ውስጥ በመግባት አደጋው የተፈጠረ እና ጥፋቱ የአመልካች ስለሆነ ሃላፊነት ያለበት አመልካች እንጂ 1ኛ ተጠሪ አይደለም በማለት መልስ አቅርበዋል፡፡ 2ኛ ተጠሪ በበኩሉ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ተመሳሳይ በሆነ መልኩ ሃላፊነት እንደሌለበት ጠቅሶ ኃላፊነት አለበት የሚባል ከሆነ ከብር 40.000 በላይ እንደማይሆን በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ አመልካች በበኩሉ የ1ኛ ተጠሪ መኪና መስመሩን ለቆ የአመልካችን መኪና በሚሽከረከርበት መስመር ገብቶ ሁለቱ ተሽርካሪዎች እንደተጋጩ፤ ለግጭቱ መከሰት ምክንያቱ የ1ኛ ተጠሪ መኪና ሹፌር እንደሆነ፣ በአደጋው ቦታ የተነሳው የቴክኒክ ምርመራ ውጤት ስለሚያስረዳ ጥፋቱ የ1ኛ ተጠሪ መኪና እንጂ የአመልካች መኪና ስላልሆነ ሃላፊነት የለብኝም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ 2ኛ ተጠሪም የተጠቀዉ የጉዳት ካሳ መጠን ተጋኗል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኂላ በሁለቱ ተሽከርካሪዎች ግጭት ምክንያት የሁለቱም መኪና ሹፌሮች ጨምሮ 18 ሰዎች የሞቱ መሆኑን እና ሁለቱም ተሽርካሪዎች ከዋናው መንገድ እስከወደቁበት ቦታ እንሸርት ያለ መሆኑን ከትራፊክ ፕላን መገንዘብ መቻሉን፣ የ1ኛ ተጠሪ አሽከርካሪ የራሱን የቀኝ መስመር ለቆ ወደ ግራ መስመር በመግባቱ በአመልካች መኪና ላይ ጉዳት ማድረሱን የቀረበው የትራፊክ አደጋ ፕላን እና የመርማሪ ፖሊስ ሪፖርት እንደሚያሳይ፣ ሁለቱ መኪኖች የተጋጩት በ1ኛ ተጠሪ መኪና መስመር ላይ እንደሆነ እና የአመልካች መኪና የራሱን መስመር ለቆ ወደ 1ኛ ተጠሪ መኪና መስመር ውስጥ ሊገባ የቻለው በመስመሩ የተጋደመ እንጨት ስለነበር ለመሸሽ ሲል እንደተጋጩ በአመልካች መኪና መስመር ላይ መውደቃቸውን ድርጊቱ ሲከሰት የነበሩ ምስክሮች ያስረዱ ሲሆን፣ በሌላ በኩል የትራፊክ ፕላን የተነሳው አደጋው ከተከሰተ ከ3 ቀን በኃላ ሲሆን መንገዱ ሀገር አቀፍ ስለሆነ በየቀኑ ብቻ ሳይሆን በየሰዓቱ በመጠንና በአይነት ብዙ ተሽርካሪ የሚያስተናግድ ከመሆኑ እና ከደረሰው ጉዳት አንጻር ፕላኑ በእለቱ እጅግ ቢዘገይ በማግስቱ አለመነሳቱ የግጭቱን መነሻ ቦታ በትክክል ለመለየት አስቸጋሪ እንደሚያደርግ፣ በአጠቃላይ 1ኛ ተጠሪም ሆነ አመልካች አደጋውን ለመቀነስ ጥረት ስለማድረጋቸው አለማስረዳታቸዉን ጠቅሶ ለደረሰው ጉዳት 1ኛ ተጠሪ እና አመልካች የጋራ ሃላፊነት አለባቸው በማለት በአጠቃላይ 273,000.00 በጋራ ለ3ኛ ተጠሪ ይክፈሉ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር የተሰኙት 1ኛ ተጠሪ እና 2ኛ ተጠሪ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዉ፣ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ በ1ኛ ተጠሪ በኩል ቀርበው የተሰሙት 2ኛ እና 3ኛ ምስክሮች ገለልተኞች ሲሆኑ አደጋው በደረሰ ጊዜ በቦታው ተገኝተው የተመለከቱ የአይን ምስክሮች በመሆናቸውና አደጋው የተፈጠረው የአመልካች አሽከርካሪ መስመሩ ላይ አጣና ስለተጋደመበት መስመሩን በመልቀቅ የ1ኛ ተጠሪ አሽከርካሪ በሚያሽከረክርበት መስመር ውስጥ ገብቶ በመጋጨቱ መሆኑን እና ተጋጭተው የቆሙት ቦታ ከግጭት በኃላ የአመልካች ተሽከርካሪ ወደ ራሱ መስመር በመንተት የደረሰበት ቦታ መሆኑን ማስረዳታቸዉን፣ በሌላ በኩል የትራፊክ ፕላኑ በተገቢው መንገድ ተጣርቶ ያልተሰራ ይልቁንም የባለሙያውን ገለልተኝነት ጥርጣሬ ላይ የሚጥል መሆኑንና ይህ ከሆነ ደግሞ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅፅ 12 በመ/ቁ/ 14981 እና 43453 እንዲሁም ቅጽ 24 መ/ቁ 175142 በሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሰረት የባለሙያ አስተያየት በምስክሮች ቃል የሚስተባበል በመሆኑ እና የ1ኛ ተጠሪ ምስክሮችም የፕላን ማስረጃውን አስተባብለው ጉዳቱ የደረሰው በአመልካች አሽከርካሪ ጥፋት ምክንያት መሆኑን የመሰከሩ በመሆኑ ለጉዳቱ ሃላፊነት ያለበት አመልካች ነው በማለት የስር ፍ/ቤት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ውሳኔን በማሻሻል አመልከች 273,000.00 ሊከፍል ይገባል ካለ በኋላ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎችን በነፃ አሰናብቷል፡፡ በአመልካች ይግባኝ አቅራቢነት ጉዳዩን የተመለከተዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም የክልሉን ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔን አጽንቶታል፡፡ ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ግንቦት 4 ቀን 2015 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤት ተፈጽመዋል ያለዉን ስህተት በመዘርዘር በዚህ ችሎት እንዲታረምለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአቤቱታቸው ይዘትም በአጭሩ የስር ፍርድ ቤቶች የአደጋው መንስኤ ንብረትነቱ የ1ኛ ተጠሪ የሆነው ተሽከርካሪ የራሱን ቀኝ መስመር ለቆ ወደ ተቃራኒ ግራ መስመር 2 ሜትር ከ33 ሳ.ሜ አልፎ ንብረትነቱ የአመልካች ከሆነው ተሽከርካሪ ጋር በመጋጨቱ አደጋው መድረሱንና ጥፋተኛ መሆኑ ከትራፊክ ጽ/ቤት እና ከተለያዩ ክፍሎች በተጻፉ ደብዳቤዎች እና በአደጋው ጊዜ በተነሳው ፕላን ተረጋግጦ እያለ አደጋው ሲፈጠር በትክክል በቦታው ስለመኖራቸው ባልተረጋገጠና በተጠና ምስክርነት የስር ፍርድ ቤት 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ኃላፊነት የለባቸውም በማለት የሰጠው ውሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መጽናቱ እንዲሁም ብር 273,000.00 አመልካች ብቻ እንድከፍል የተሰጠው ውሳኔ በማስረጃ ያልተደገፈ ከመሆኑም በላይ አከፋፈሉም በርትዕ የታየ ባለመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል በማለት ታርሞ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የሰበር አቤቱታዉ በሰበር ችሎቱ ተመርምሮም የትራፍክ ፖሊስ ፕላንና የሙያ ማስረጃ እንዲሁም ከተለያዩ ክፍሎች የተጻፉት ማስረጃዎች ታልፈው ለደረሰው አደጋ ኃላፊነት ያለበት አመልካች ነው ተብሎ መወሰኑ ህጉን የተከተለ መሆን አለመሆኑን አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል ተብሏል፡፡ በዚሁም መሠረት ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት በሚል መጥሪያ ተልኮላቸው 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች መጥሪያ ተቀብለው መልስ ለመቀበል በተያዘው ቀጠሮ ባለመቅረባቸው መልስ የማቅረብ መብታቸው ታልፏል፡፡ 1ኛ ተጠሪ ታህሳስ 23 ቀን 2016 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ የባለሙያን ማስረጃ በበቂ ሁኔታ አስተባብዬ ያረጋገጥኩ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ በአግባቡ ነው፡፡ ለአደጋው መንስኤም ሆነ ትክክለኛ ጥፋተኛ የአመልካች ተሽከርካሪ መሆኑ በበቂ ሁኔታ የተረጋገጠ ስለሆነ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር በ1ኛ ተጠሪ መልስ ላይ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከላይ የተገለፀውን ሲመስል ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉን ዉሳኔ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ጉዳት ስለመድረሱ እንዲሁም አደጋዉ የተከሰተዉ የአመልካች እና የ1ኛ ተጠሪ ተሽከርካሪዎች በመጋጨታቸዉ ምክንያት ስለመሆኑ ግራ ቀኝን አላከራከረም፡፡ አመልካች በሰበር አቤቱታቸዉ እንጠቀሱት አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ በጋራ ብር 27,850 በአደጋዉ ምክንያት ህይወታቸዉ ላለፉት ሰዎች ወጪ መክፈላቸዉ መረጋገጡም 1ኛ ተጠሪ ኃላፊነቱን ማመኑን የሚያሳይ አይደለም፡፡ በመሆኑም ግጭቱ የተከሰተዉ ከሁለቱ ተሽከርካሪዎች በየትኛዉ ተሽከርካሪ ጥፋት ምክንያት ነዉ? የሚለዉ ነጥብ አከራካሪ ነዉ፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንኑ በጭብጥነት በመያዝ ግራ ቀኝ ያቀረቧቸዉን የሰዉ ምስክሮች እንዲሁም ከትራፊክ ፖሊስ የቀረበዉን የአደጋ ሪፖርት መሠረት በማድረግ መርምሮ ለደረሰዉ ጉዳት ሁለቱም ተሽከርካሪዎች

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የየራሳቸዉ አስተዋጽዖ ያላቸዉ ስለመሆኑ ተረጋግጧል በሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ ሁለቱም በጋራ ኃላፊነት አለባቸዉ በሚል የወሰነ ሲሆን፣ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በበኩሉ በከፍተኛ ፍርድ ቤት የቀረቡትን የሰዉ እና የሰነድ ማስረጃ (የትራፊክ ሪፖርት) በድጋሚ መርምሮ እና መዝኖ ለደረሰዉ አደጋ መንስኤዉ የአመልካች ተሽከርካሪ አሽከርካሪ በፈጸመዉ ጥፋት ምክንያት ነዉ በሚል የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡

የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዚህ ድምዳሜ ላይ የደረሰዉም 1ኛ ተጠሪ እራሳቸዉ እንዲሁም 4ኛ እና 5ኛ ምስክሮች የትራፊክ ፕላኑ በአድልኦ የተሰራ እንጂ በትክክለኛ ማስረጃ ላይ ተመስርቶ ያልተሰራ መሆኑን በማረጋገጥ መመስከራቸዉን፤ ገለልተኞች የሆኑ እና አደጋዉ በደረሰ ጊዜ በቦታዉ ተገኝተዉ የተመለከቱ የ1ኛ ተጠሪ 2ኛ እና 3ኛ ምስክሮች የአመልካች አሽከርካሪ መስመሩ ላይ አጠና ስለተጋደመበት መስመሩን በመልቀቅ የ1ኛ ተጠሪ አሽከርካሪ በሚያሽከረክርበት መስመር ዉስጥ ገብቶ በመግጨቱ መሆኑን እና ተጋጭተዉ የቆሙበት ቦታ ከግጭቱ በኋላ የአመልካች ተሽከርካሪ ወደ ራሱ መስመር በመትተት የደረሰበት ቦታ መሆኑን ማስረዳታቸዉን፣ ፕላኑም በተገቢዉ መንገድ ተጣርቶ ያልተሰራ ይልቁንም የባለሙያዉን ገለልተኝነት ጥርጣሬ ዉስጥ የሚከት መሆኑን ያሳያል የሚል ምክንያት በመጥቀስ ስለመሆኑ የዉሳኔዉ ይዘት ያሳያል፡፡ ይህ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ድምዳሜ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከቱት ሁለቱ ፍርድ ቤቶች ከላይ በተመለከተዉ የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ ሲደርሱ ከማስረጃ አቀባበልና ምዘና መርህ ጋር በተያያዘ የፈጸሙት ስህተት ስለመኖሩ ዉሳኔዉ አያሳይም፡፡ በርግጥ በማስረጃ እንዲረጋገጥ የተያዘዉ የፍሬ ነገር ጭብጥ ከሙያ ጋር የተገናኘ እንደሆነ እና የባለሙያ ማስረጃ የቀረበ እንደሆነ፣ በምዘና ወቅት ከሌሎች ማስረጃዎች ይልቅ የባለሙያ ማስረጃ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠዉ ነዉ፡፡ ይሁንና የቀረበዉን የባለሙያ ማስረጃ ገለልተኝነት እና ብቃት ጥያቄ ዉስጥ የሚያስገባ ምክንያት ካለ በሌሎች ማስረጃዎች ሊስተባበል እንደሚችል ይታወቃል፡፡ ይህን አስመልክቶ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም የሰ/መ/ቁጥር 175142 (በቅጽ 24 ላይ የታተመዉ) ጨምሮ በሌሎች በርካታ መዛግብት ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ ስለሆነም የተያዘዉን ጉዳይ በይግባኝ የተመለከቱት ሁለቱ ፍርድ ቤቶች የቀረበዉ የትራፊክ ሪፖርት ገለልተኛ አለመሆኑን ከግምት ዉስጥ በማስገባት የሰዉ ምስክሮችን ቃል መሠረት በማድረግ የደረሰዉ አደጋ በአመልካች ተሽከርካሪ አሽከርካሪ ጥፋት ምክንያት ነዉ በሚል ድምዳሜ ላይ መድረሳቸዉ ለቀረቡት ማስረጃዎች ተገቢዉን ዋጋ አልሰጡም የሚያሰኝ አይደለም፡፡

በሌላ በኩል በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80 (3/ሀ) ላይ በግልጽ እንደተመለከተዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉን ዉሳኔዎች በማረም ላይ የተገደበ ነዉ፡፡ መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት ነዉ? ወይም አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ መቼ ነዉ? የሚለዉን ጽንሰ ሃሳብ አስመልክቶ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ትርጓሜ ይሰጣል፡፡ በአዋጁ በትርጉም ክፍል አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለዉ አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን፣ ህግ ያላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉን ህግ የሚጠቅስ፣ ለክርክሩ አግባብነት ያለዉ ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለዉ ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፣ በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ዉድቅ በማድረግ የተወሰነ፣ በፍርድ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አፈፃፀም ሂደት ከዋናዉ ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትዕዛዝ የተሰጠበት፣ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተወሰነ፣ የአስተዳደር አካል ወይም ተቋም ከህግ ዉጭ የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ በመቃረን የተወሰነ ሲሆን ነዉ፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በሚል የሰበር አቤቱታ ሲቀርብለት ለአቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ ጉዳይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ ከላይ በዝርዝር ከተመለከቱት ሁኔታዎች ዉስጥ ቢያንስ አንዱን ያሟላ ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 10 ላይ ከተመለከቱት ድጋጌዎች የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡

ከዚህ ሁሉ አንፃር ሲታይ ለደረሰዉ ጉዳት ኃላፊነት ያለበት አመልካች ነዉ በሚል የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠዉን ዉሳኔ በማጽናት በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በተሰጠዉ ዉሳኔ ላይ የተፈጸመ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡ ስለሆነም የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

**<u>ዉሳኔ</u>**

1. የአማራ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 01-21523 ላይ ጥቅምት 05 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት እንዲሁም ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 217486 ላይ የካቲት 30 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጡት ዉሳኔ በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1) መሠረት ጸንተዋል፡፡
2. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፍ/ደ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁጥር---246931

ቀን- ጥቅምት 06 ቀን 2017 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ብርሃኑ መንግስቱ

ማርታ ተካ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ መድኅኔ ወርቃለማሁ - አልቀረቡም

**ጠሪዎች፡-** 1. ወ/ሮ ባለምዙሪያ ዘርጋዉ - አልቀረቡም

2. ጌታቸዉ ወልዱ ሪልስቴት (ሰንራይዝ ሪልስቴት) / ጠበቃ ታምሩ ታደሰ ቀረቡ

3. አቶ ጌታቸዉ ወልዱ (ሥራ አስኪያጅ)

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ጉዳዩ የክርክር ወጪና ኪሳራን የተመለከተ ሲሆን የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍ/ቤት 1ኛ ተጠሪ ከሳሽ፤ 2ኛ እና 3ኛ ተጠረዎች ተከሳሾች ሲሆኑ አመልካች ደግሞ የመቃወም አመልካች ነበሩ፡፡ የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 137940 ጥቅምት 30 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በተሰጠ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ትዕዛዝ የጸናዉ ወጪና ኪሳራ የተመለከተዉ የዉሳኔ ክፍል መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በሚል ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ፡- 1ኛ ተጠሪ በ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት ክስ መነሻነት ለክርክር መነሻ የሆነዉን አፓርታማ ቤት ለ1ኛ ተጠሪ እንዲያስረክቡ ግንቦት 10 ቀን 2014 ዓ.ም ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡ አመልካች ይህ ዉሳኔ የተሰጠበትን አፓርታማ ቤት በብር 5,658,770 ከ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ላይ መጋቢት 17 ቀን 2013 ዓ.ም በተደረገ ዉል መግዛታቸዉንና ስመ ሀብት ተዛዉሮላቸዉ የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ ያወጡበትን ቤት እንዲያስረክቡ መወሰኑ ተገቢ አለመሆኑንና ዉሳኔ መሰጠቱን ያወቁት ቤቱን እንዲያስረክቡ የአፈጻጸም ማመልከቻ ሲደርሳቸዉ መሆኑን በመግለጽ ዉሳኔዉ እንዲሰረዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 መሰረት የመቃወም አቤቱታ ሲያቀርቡ በክርክሩ ምክንያት ያወጡት ወጪ በመቃወም ተጠሪዎች እንዲተኩላቸዉ እንዲወሰን ጠይቀዋል፡፡ 1ኛ ተጠሪ አስቀድሞ የተሰጠዉ ፍርድ እንዲጸናና የአመልካች መቃወሚያ ዉድቅ ሊደረግ ይገባል ያሉባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር ክርክር ያቀረቡ ሲሆን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በበኩላቸዉ ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉን ቤት ለአመልካች የሸጡላቸዉ 1ኛ ተጠሪ የዉል ግዴታቸዉን ባለመወጣታቸዉ ዉሉን መፍረሱን ከገለጹላቸዉ በኃላ በመሆኑ አመልካች አስቀድሞ የተሰጠዉ ዉሳኔ እንዲሰረዝ ያቀረቡት የመቃወም አቤቱታ ተገቢ መሆኑን በመግለጽና በመደገፍ አስተያየታቸዉን ሰጥተዋል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮና መርምሮ፡- 2ኛ ተጠሪ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ሰኔ 21 ቀን 2011 ዓ.ም የተደረገዉ የቃብድ ዉል ክፍያዉን በተቀመጠዉ የጊዜ ገደብ ባለመክፈላቸዉ ዉሉ ፈርሷል የሚሉ ቢሆንም በዉሉ የተቀመጠዉ ጊዜ ካለፈ በኃላም በስምምነቱ መሠረት ክፍያ ከ1ኛ ተጠሪ ተቀብሎ ደረሰኝ መስጠቱ ዉሉን እንዳስቀጠለ የሚያስቆጥረዉ በመሆኑ በመካከላቸዉ ያለዉ ስምምነት ቀርቷል ለማለት የሚቻል አለመሆኑን፤ ሆኖም የቃብድ ሽያጭ ዉሉ ስልጣን ባለዉ አካል ወይም በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት ያልተደረገና ያልተመዘገበ በመሆኑ አስገዳጅነቱ በተዋዋዮች መካከል ብቻ እንጂ የ3ኛ ወገኖችን መብት የሚገድብ ባለመሆኑ ከአመልካች ጋር መጋቢት 17 ቀን 2013 ዓ.ም የተደረገዉ የሽያጭ ዉል በሕግ አግባብ በዉል አዋዋይ ፊት የተደረገና ስመ-ሀብት ዝዉዉር የተደረገበት በመሆኑ ሊፈርስ የሚችልበት የሕግ አግባብ ባለመኖሩ የአመልካችን መቃወሚያ ተቀብሎ አስቀድሞ ግምቦት 10 ቀን 2014 ዓ.ም 1ኛ ተጠሪ ቤቱን እንዲረከቡ የሰጠዉን ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ 360 መሰረት ሲሰርዝ 1ኛ ተጠሪ የከፈሉትን ገንዘብና ሌሎች ኪሳራዎች ከ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የመጠየቅ መብታቸዉን በመጠበቅ እንዲሁም ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸዉን ይቻቻሉ በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች ወጪና ኪሳራን አስመልክቶ ግራ ቀኙ የየራሳቸዉን ይቻቻሉ ተብሎ በተሰጠዉ የዉሳኔ ክፍል ቅር ተሰኝተዉ ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ዉሳኔዉ በትዕዛዝ ጸንቷል፡፡ የሰበር አቤቱታዉም ሊቀርብ የቻለዉ ይህ የዉሳኔዉ ክፍል መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በሚል ነዉ፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡- 1ኛ ተጠሪ ክሱን ሲያቀርቡ ቤቱ በአመልካች እጅ የሚገኝና አስፈላጊዉ ሕጋዊ ማስረጃ ያላቸዉ መሆኑን እያወቁ ንብረታቸዉን አላግባብ ለመዉሰድ ክስ ማቅረባቸዉ፤ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ቤቱን ሲሸጡላቸዉ የኔ ነዉ ባይ ተቃዉሞ ቢመጣ ክሱን በራሳቸዉ ወጪ ለመመለስና ዉሉ በነበረበት እንዲቀጥል ዋቢ መሆናቸዉንና ግዴታ ገብተዉ እያለ 1ኛ ተጠሪ ሲከሷቸዉ ተገቢዉን ክርክር በማድረግና አመልካችም በክሱ ዉስጥ በተከሳሽ በኩል ጣልቃ ገብ ሆነዉ በክርክሩ እንዲካተቱ ማድረግ ሲገባቸዉ አመልካች ባለወቁበት በዝምታ ሲከራከሩ ቆይተዉ እንዲያስረክቡ ዉሳኔ ተሰጥቶ በአፈጻጸም ሲገደዱ ቤቱ ሊወሰድ ነዉ የመቃወም አቤቱታ አቅርበዉ መብታቸዉን እንዲያስከብሩ ባሳወቋቸዉ መሠረት ወደ ክርክሩ ገብተዉ ዉሳኔዉን ማስለወጥ ቢችሉም በክርክሩ ምክንያት ለዳኝነትና ለጠበቃ ያወጡትን ወጪ እንዲተኩ ሊወሰን ሲገባ ተቻቻሉ ተብሎ መወሰኑ ፍትሐዊ ባለመሆኑና መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ አመልካች ያወጡትን ወጪ ተጠሪዎች ባልተነጣጠለ ኃላፊነት እንዲተኩ እንዲወሰን የሚጠይቅ ነዉ፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የክርክር መነሻ የሆነዉን ቤት አመልካች ገዝተዉና ተረክበዉ በነበሩበት ሁኔታ በተጠሪዎች መካከል የነበረዉን ክርክር አዉቀዉ የክርክር ተካፋይ እንዲሆኑ በተጠሪዎች ባልተደረገበት ዉሳኔ ተሰጥቶ በአፈጻጸም ጉዳዩን አዉቀዉና ሳልተገባ ክርክር ተዳርገዉ ዉሳኔዉ ባሻሩበት ሁኔታ በስር ፍ/ቤቶች ግራ ቀኙ የየራሳቸዉን ወጪና ኪሳራ ይቻሉ ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 462 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ዓላማ እና በዚህ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 91103 ከተሰጠዉ ገዥ ትርጉም አንጻር ለማጣራት ጉዳዩ በሰበር ችሎት እንዲታይ የተደረገ ነዉ፡፡

1ኛ ተጠሪ ሚያዚያ 30 ቀን 2016 ዓ.ም የተዘጋጀ 2 ገጽ መልስ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱ በአጭሩ፡- የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 462 ጉዳዩን ለሚያየዉ ፍ/ቤት ወጪን አስመልክቶ የመወሰን ሙሉ ስልጣን ሰጥቶታል፡፡ በሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 91103 የተሰጠዉ ዉሳኔ ለትርጉሙ መነሻ ያደረገዉ የተከራካሪዎችን የቅን ልቦና መጓደል ወይም ክርክራቸዉ የማይገባ ጥያቄ ሲሆን መሆኑንና 1ኛ ተጠሪ በአንጻሩ በ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በፈጸሙት ቅን ልቦና የጎደለዉ አካሄድ የተበደሉ በመሆናቸዉ መብታቸዉን ለማስከበር ተንቀሳቅሰዋል፡፡ የስር ፍ/ቤት የአመልካችን የቤቱን ባለቤትነት መብት በአንድ በኩል ሲያረጋግጥ፤ በሌላ በኩል በተጠሪዎች መካከል የነበረዉ ዉል ያልፈረሰ መሆኑን በማጽናት የ1ኛ ተጠሪን መብት ጠብቋል፡፡ በስር ፍ/ቤት 1ኛ ተጠሪ ክሱን ሲመሰርቱ አመልካች ያወቁ መሆናቸዉን አላረጋገጠም፤ ሊያረጋግጥም አይችልም፡፡ ስለሆነም አመልካች ወጪና ኪሳራ 1ኛ ተጠሪ ጭምር እንዲከፍሉ እንዲወሰን ያቀረቡት አቤቱታ ክፍል ዉድቅ እንዲደረግላቸዉ በመጠየቅ ተከራክረዋል፡፡

2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በበኩላቸዉ ሚያዚያ 15 ቀን 2016 ዓ.ም የተዘጋጀ መልስ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፡- 1ኛ ተጠሪ ቤቱን ለመግዛት የቀብድ ዉል የፈጸሙ ቢሆንም በዉሉ መሰረት ግዴታቸዉን ባለመወጣታቸዉ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ለሌላ ወገን የተሸጠ በመሆኑ የመጠየቅ መብት የላቸዉም በማለት መልስ ሰጥተዉ፣ አመልካች ወደ ክርክሩ ጣልቃ ገብተዉ እንዲከራከሩ ለማድረግ ጥረት ያደረጉ ቢሆንም አመልካች በሀገር ዉስጥ ስላልነበሩ ለማገኘት ባለመቻላቸዉ ዉሳኔ ተሰጥቶ ወዲያዉኑ አፈጻጸም ሲከፈቱ የአመልካች ተወካይ መኖራቸዉን ሰምተዉ የመቃወም አቤቱታ እንዲያቀርብ ያስደረጉ በመሆኑ ጥፋት የለባቸዉም፡፡ የስር ፍ/ቤት የመቃወም አቤቱታዉ ዉሳኔ ሲሰጥ ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ በማለት ትዕዛዝ የሰጠዉ በሁሉም ላይ የደረሰዉን ወጪና ኪሳራ በማመዛዘን በመሆኑ ተገቢ ነዉ፡፡ ወጪና ኪሳራ ሊከፈል ይገባል ቢባል እንኳ ሊወሰን የሚገባዉ በ1ኛ ተጠሪ ላይ እንጂ በሌሎች ላይ ሊሆን አይገባም፡፡ አመልካች ከ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች እርስ በርስ ያልተካሰሱ በመሆኑ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ባልተነጣጠለ ኃፊነት የሚከፍሉበት ምክንያት የለም፡፡ ሁሉም ተጠሪዎች የመክፈል ኃላፊነት አለባቸዉ ቢባል እንኳ የድርሻቸዉን እንጂ ከ1ኛዋ ተጠሪ ጋር ባልተነጣጠለ ኃላፊነት የሚከፍሉበት አግባብ የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካች ሚያዚያ 30 ቀን 2016 ዓ.ም ግንቦት 07 ቀን 2016 ዓ.ም የተዘጋጁ የሰበር አቤቱታቸዉን በሚያጠናክር መልኩ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን እኛም አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡ የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር መርምረን እንደተረዳነዉ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሻዉ ጭብጥ፡- የክርክር መነሻ የሆነዉን ቤት አመልካች ገዝተዉና ተረክበዉ በነበሩበት ሁኔታ በተጠሪዎች መካከል የነበረዉን ክርክር አዉቀዉ የክርክር ተካፋይ እንዲሆኑ በተጠሪዎች ባልተደረገበት ዉሳኔ ተሰጥቶ በአፈጻጸም ጉዳዩን አዉቀዉና ላልተገባ ክርክር ተዳርገዉ ዉሳኔዉ ባሻሩበት ሁኔታ በስር ፍ/ቤቶች ግራ ቀኙ የየራሳቸዉን ወጪና ኪሳራ ይቻሉ ተብሎ በስር ፍ/ቤት የተሰጠዉ የዉሳኔ ክፍል ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 462 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ዓላማ እና በዚህ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 91103 ከተሰጠዉ ገዥ ትርጉም አንጻር ተገቢ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነዉ፡፡

በመሠረቱ ፍርድ ከተጻፈ የፍርዱ ተፈጻሚነት ያለዉ ክፍል በትዕዛዝ መልክ ሆኖ ከሚገለጹበት ነገሮች ዉስጥ አንዱ ክሱ ወይም ይግባኙ ያስከተለዉን ወጭ ማን እንደሚከፍል መስሎ የታየዉን ትዕዛዝ መስጠት እንደሚችል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 183(1/ሠ) ስር የተደነገገ ሲሆን ዝርዝር አወሳሰኑን በተመለከተ ደግሞ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 462 ስር በሌላ አኳኃን እንዲፈጸም በግልጽ ካልተደነገገ በቀር በክስ ምክንያት ስለሚከፈለዉ ስለማናቸዉም ወጭና ኪሳራ የሚከፍለዉን ወገን፣ የወጭንና የኪሳራዉን ልክ፣ የሚከፈልበትን የሀብት ምንጭ፣ የአከፋፈሉን ሁኔታ ሌላዉንም ተገቢ መስሎ የታየዉን ዉሳኔ ወይም ትዕዛዝ ፍርድ ቤቱ ትክክል መስሎ በሚገምተዉ ሁኔታ ሊሰጥ ይችላል በማለት ደንግጓል፡፡ በተለይ ተረቺዉ ለረቺዉ ኪሳራና ማናቸዉንም ወጭ እንዲከፍል ፍርድ ቤቱ ሲያዝ ወጭ ያደረገዉ ወገን የወጭዉን ልክ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የሚያሳይ ዝርዝር አዘጋጅቶ ማቅረብ እንዳለበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጅ/ቁ 463(1) ስር ተመልክቷል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለዉ በመርህ ደረጃ የረቺን የክርክር ወጭን ተረቺ እንዲከፍል ማድረግ ሲሆን ሆኖም ፍ/ቤት የረቺ ክርክር ወጪዎች እንዲሸፈኑ ወይም እንዳይሸፈኑ የመወሰን ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡ ይህ ማለት ግን ፍ/ቤቱ እንደፈለገዉ ይወስናል ማለት ሳይሆን በምክንያትና ፍትሕን መሠረት አድርጎ ሊወሰን ይገባል፡፡ በተለይ ከቅን ልቦና ውጪ ለክርክር የተጋበዘውን ወገን በተመለከተ የክርክሩ ረቺ መሆኑ እስከታወቀ ድረስ ቅን ልቦና ከሌለው ወገን በክርክሩ ምክንያት ያወጣውን ወጪ እንዲተካለት ማድረግ ክርክሮች ያላግባብ እንዳይፈጠሩ የማድረግ ውጤት ያለው በመሆኑ ተግባራዊ ሊደረግ የሚገባው መሆኑን የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 91103 አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች በዉል አዋዋይ ፊት ተዋዉለዉ የገዙትንና ስመ-ሀብቱን አዛዋዉረዉ በራሳቸዉ ስም የባለሀብትነት ማረጋገጫ ያወጡበትን ቤታቸዉን የክርክሩ ተከፋይ ባልሆኑበት 1ኛ ተጠሪ እንዲረከቡ በመወሰኑ ይህን ዉሳኔ ለማሰረዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 መሠረት የመቃወም አቤቱታ አቅርበዉ ዉሳኔዉን አስሰርዘዉ ረቺ ሆነዋል፡፡ 1ኛ ተጠሪ በበኩላቸዉ በ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ላይ ክስ የመሠረቱት በተጠሪዎች መካከል ብቻ ግዴታ በሚጥል ሰኔ 21 ቀን 2011 ዓ.ም በተደረገ የአፓርትመንት መኖሪያ ቤት ሽያጭ ለመፈጸም በተደረገ የቀብድ የሽያጭ ዉል ስምምነት መሠረት እንደዉሉ እንዲፈጸምላቸዉ እንጂ 3ኛ ወገን በሆነዉ አመልካች ላይ የመሠረቱት ክስ አልነበረም፡፡ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በቀብድ ዉል ስምምነቱ መሠረት በየወቅቱ የሚከፈለዉን ክፍያ የመክፈል ግዴታቸዉን 1ኛ ተጠሪ በለመወጣታቸዉ ስምምነቱን በ1ኛ ተጠሪ ጥፋት አስቀድሞ ያቋረጡና ቤቱን ለ3ኛ ወገን የሸጡ መሆኑን በመግለጽ የተከራከሩ ቢሆንም የስር ፍ/ቤት ዉሉ አስቀድሞ በ1ኛ ተጠሪ ጥፋት አልፈረሰም ያለበትን ምክንያት በመግለጽ ለ1ኛ ተጠሪ ቤቱን በማስረከብ እንደዉሉ እንዲፈጽሙ ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ፍ/ቤቱ የሰጠዉ ምክንያትም ሆነ ዉሳኔዉ ተገቢ አይደለም በሚል ይግባኝ ጠይቀዉ ዉሳኔዉን ወይም ምክንያቱን ያስቀየሩበት ሁኔታ ስለመኖሩ የተገለጸ ነገር የለም፡፡ እንዲሁም 1ኛ ተጠሪ ክስ ከማቅረባቸዉ በፊት ቤቱ በሽያጭ 3ኛ ወገን ለሆኑት አመልካች በሽያጭ መተላለፉንና እንደዉሉ ሊፈጸምላቸዉ እንደማይችል እያወቁ ቤቱን ለመረከብ ከቅን ልቦና ዉጭ ክስ አቅርበዋል እንዳይባል ከክስ በፊት ይህን እንደሚያዉቁ በሌሎች ተከራካሪዎች የቀረበ ክርክር ባለመኖሩ ቤቱን ለመረከብ አስቀድሞ የተሰጠላቸዉ ዉሳኔ ቢሰረዝባቸዉም አመልካችን ከቅን ልቦና ዉጭ ለክርክር የዳረጉበት ሁኔታ ባለመኖሩ 1ኛ ተጠሪ የአመልካችን የክርክር ወጭ እንዲከፍሉ ተብሎ በስር ፍ/ቤት ዉሳኔ አለመሰጠቱ የሚነቀፍ ባለመሆኑ 1ኛ ተጠሪን አስመልክቶ አመልካች ያቀረበዉን የሰበር አቤቱታ አልተቀበልንም፡፡

በሌላ በኩል 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችን አስመልክቶ የቀረበዉን ቅሬታ በተመለከተ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች አስቀድመዉ ቤቱን ለ1ኛ ተጠሪ በሽያጭ ዉል ለማስተላለፍ የፈጸሙት የቀብድ ሽያጭ ዉል ስምምነት በአግባቡ ባልፈረሰበት ሁኔታ ለአመልካች በሽያጭ ዉል ያስተላለፉ በመሆናቸዉ ከሽያጭ ዉሉ በፊት በቤቱ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ላይ መብት መስርቻለሁ የሚል ወገን ሲቀርብ በዋቢነት አልፈዉ በራሳቸዉ ወጭ የአመልካችን መብት የማስከበር የዉል ግዴታ ያለባቸዉ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ቤቱን ለመረከብ 1ኛ ተጠሪ ክሱን ሲያቀርቡ በ1ኛ ተጠሪ ጥፋት የቀብድ ሽያጭ ዉሉ መፍረሱን ወይም ቤቱ ለሌላ 3ኛ ወገን በመተላለፉ ዉሉ ሊፈጸም እንደማይችል በማስረዳት በስር ፍ/ቤትም ሆነ በየደረጃዉ ባሉት ፍ/ቤቶች ተከራክሮ በመርታት የአመልካችን መብት ማስከበር ባለመቻላቸዉ አመልካች የመቃወም አቤቱታ ለማቅረብ በመገደዱ ላልተገባ የክርክር ወጪ መዳረጉ አከራካሪ አይደለም፡፡ እንዲሁም የአመልካችን የክርክር ተካፋይነት ማስቀረት ባይችሉ እንኳ ቤቱ በሽያጭ ለአመልካች መተላለፉንና አመልካች ባልተሳተፉበት የሚሰጠዉ ፍርድ መብታቸዉን ሊነካ እንደሚችል በመግለጽ አመልካች ጣልቃ እንዲገቡ ፍ/ቤቱን በመጠየቅ ወይም አመልካችን በማስታወቅ ጣልቃ ለመግባት እንዲጠይቁ በማስደረግ ወጭን መቀነስ እየቻሉ ባለማድረጋቸዉ ዉሳኔ ተሰጥቶ ዉሳኔዉን ለማስረዘዝ አመልካች የመቃወም አቤቱታ ለማቅረብ ተገድደዋል፡፡ አመልካች በሀገር ዉስጥ ያልነበሩ በመሆናቸዉ በወቅቱ ልናሳዉቃቸዉ አልቻልንም የሚለዉም ክርክር ቢሆን በኃላ ላይ አፈጻጸሙ ሲቀርብ የአመልካችን ተወካይ ፈልገዉ ያሳዉቁ መሆናቸዉን ራሳቸዉ የገለጹ ስለሆነ ተገቢነት ያለዉ አይደለም፡፡ ስለሆነም በ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ድክመት ወይም ቸልተኝነት አመልካች ለክርክር ተዳርገዉ ያወጡትን የክርክር ወጭ በስር ፍ/ቤት እንዲተኩ ያለመወሰኑ የዉልም ሆነ የህግ መሠረት የሌለዉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 462 እና ተከታዮችን ድንጋጌዎች እንዲሁም በሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 91103 የተሰጠዉን ትርጉም ያላገናዘበ በመሆኑ ስህተቱ ሊታረም የሚገባዉ ነዉ፡፡

የክርክር ወጭዉን መጠን ወይም አመልካች ምን ያህል ወጭ ሊተካላቸዉ ይገባል የሚለዉን በተመለከተ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 463(1) መሠረት የወጭ ዝርዝር ለስር ፍ/ቤት አቅርበዉ ሊያስወስኑ የሚገባዉ እንጂ በዚህ ሰበር ደረጃ የሚወሰን ባለመሆኑ ለስር ፍ/ቤት እንዲያቀርቡ መፍቀዱ ተገቢ ይሆናል፡፡

ሲጠቃለል 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ሰኔ 21 ቀን 2011 ዓ.ም በተደረገ ቀብድ ዉሉ መሠረት 1ኛ ተጠሪ የመክፈል ግዴታቸዉን በወቅቱ ባለመወጣታቸዉ አስቀድሞ ዉሉ ከፈረሰ በኃላ ለአመልካች ቤቱ በሽያጭ መተላለፉን በማስረዳት ወይም የቀብድ ስምምነቱ መሠረት የሽያጭ ዉሉ ሊፈጸም እንደማይችል በማስረዳት የአመልካችን መብት ሊያስጠብቁ ባለመቻላቸዉ ወይም የክሱን መቅረብ ወዲያዉኑ ለአመልካች በማሳወቅ የክርክሩ ተከፋይ ሆነዉ መብታቸዉን እንዲያስጠብቁ ባለማድረጋቸዉ አመልካች የመቃወም አቤቱታ አቅርበዉ በቤታቸዉ ላይ የተሰጠዉን ዉሳኔ ባስሰረዙበት ሁኔታ የአመልካች የክርክር ወጭ በ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች እንዲከፈል በስር ፍ/ቤቶች አለመወሰኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 462 እና ተከታዮችን ድንጋጌዎች ዓላማ እንዲሁም ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 91103 የሰጠዉን ገዥ ትርጉም ያላገናዘበ በመሆኑ በፌዴራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ለ እና ሸ) እና 10(1/ሀ) መሰረት መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

## ዉሳኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 137940 ጥቅምት 30 ቀን 2015 ዓ.ም ተሰጥቶ፤ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 302501 የካቲት 25 ቀን 2015 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ የጸናዉ ወጪና ኪሳራን አስመልክቶ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1/ሀ) መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የአመልካችን የክርክር ወጭ ሊተኩ ይገባል ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. አመልካች በስር ፍ/ቤት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለባቸዉን የወጪ ዝርዝር ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቅርበዉ የማስወሰን መብት አላቸዉ ተብሎ ተወስኗል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. 1ኛ ተጠሪን አስመልክቶ የስር ፍ/ቤት ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ በማለት የሰጠዉ የዉሳኔ ክፍል ጸንቷል፡፡ ሌላዉ የዉሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡
5. ግራ ቀኙ በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ.መ.ቁ.246938

ጥቅምት 06 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች፡...... 1. ብርሃኑ አመነዉ

2. በእዉቀት በላይ

3. ቀነዓ ቂጣታ

4. ብርሃኑ መንግስቱ

5. ማርታ ተካ

አመልካች፡ ........የሀላባ ቁሊቶ ከተማ ማዘጋጃ ቤት የቀረበ የለም

ተጠሪ፡.............አቶ ካሳ ጉንቲራ የቀረበ የለም

ይህ መዝገብ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

**ፍርድ**

ይህ የከተማ ይዞታ ክርክር የተጀመረዉ በሀላባ ቁልቶ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች የሥር ተከሳሽ፣ የአሁን ተጠሪ የሥር ከሳሽ ሆኖ ሲከራከሩ ነበር። ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ አመልካቾች የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.78161 መጋቢት 7 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት በማመልከቱ ነዉ።

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ የአሁን ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት ባቀረቡት የክስ አቤቱታ፡ አመልካች በቁሊቶ ከተማ ዞቤቻሜ ክ/ከተማ ዉስጥ ለኢንቨስትመንት የሰጠኝ እና ካርታ ያገኘሁበትን መጠኑ 4730.5 ካ.ሜ የሆነዉን ይዞታ ተገቢዉን ካሳ ሳይከፍለኝ እ ምትክ ቦታ ሳይሰጠኝ ሊያስለቅቀኝ እያስገደደኛ ስለሆነ ቀደም ሲል

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ያልተገሙቱ ንብረቶች በባለሙያ ተገምቶ ወቅቱን ባገናዘብ ዋጋ እና ምትክ ቦት እንዲሰጠኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

የአሁን አመልካች በዚህ ክስ ላይ መልስ እንዲሰጥ መጥሪያ ተለጥፎ ሊቀርብ ባለመቻሉ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ በመስጠት፣ የተጠሪን ክስና ማስረጃ በመመርመር በሰጠዉ ዉሳኔ ተጠሪ ለክርክር ምክንያት የሆነዉ ይዞታ ለኢንቨስትመንት የተሰጠዉ መሆኑ በቀረበዉ ማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ፣ ተጠሪ ዘርዝሮ ያቀረባቸዉ ንብረቶች ተመጣጣኝ ካሳ እንዳልተከፈለዉ በማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ፣ እነዚህ ንብረቶች በባለሙያ በወቅቱ ዋጋ ተገምቶ ካሳ እንዲከፈለዉ እና ለተወሰነዉ ኢንቨስትመንት ቦታዉ ተመጣጣኝ ምትክ ቦታ እንዲሰጠዉ በማለት ፍ/ቤቱ ወስኗል፡፡

ከዚህ በኋላ የአሁን አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.6 መሰረት ባቀረበዉ አቤቱታ ተጠሪ ይህን ዉሳኔ ያሰጠዉ ከማዘጋጃ ቤት ሰራተኞች ጋር ተመሳጥሮ ማረጋገጫ በማሰራትና ሐሰተኛ ማስረጃ በማቅረብ በወንጀል ጠቀስ ማስረጃ በመሆኑ ዳግም ዳኝነት እንዲታይልን በማለት አመልክቷል፡፡ የአሁን ተጠሪ በበኩሉ ባቀረበዉ ክርክር አመልካች ያቀረበዉ የዳግም ዳኝነት ጥያቄ የሕግ መሰረት የለዉም፣ ቀደም ሲል የተሰጠዉ ዉሳኔ በሐሰት ተዘጋጅቶ የቀረበዉን የሰነድ ወይም ሐሰተኛ የምስክርነት ቃል ወይም ወንጀል ጠቀስ የሆነ ተግባርን መሰረት ያደረገ ስለሆነ ተቀባይት የለዉም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር በመመርመር በሰጠዉ ብይን አመልካች ያቀረበዉ አቤቱታ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.6 የሚያሟላ በመሆኑ ጉዳዩ በዳግም ዳኝነት ሊታይ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን ተጠሪ በዚህ ብይን ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ችሎቱም ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ አመልካች ባቀረበዉ አቤቱታ ተጠሪ ፍርድ ያገኘበትንና ሐሰተኛ የተባለዉን ማስረጃ ያላቀረበ በመሆኑ፣ ያቀረበዉ የዳግም ዳኝነት ይታይልን ጥያቄ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.6 ሥር የተመለከቱትን መስፈርቶችን የማያሟላ በመሆኑ፣ አመልካች በቂ ማስረጃ ያላቀረበ በመሆኑ ጉዳዩ በዳግም ዳኝነት ሊታይ አይገባም በማለት የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠዉን ብይን በመሻር ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች በ30/8/2015 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ በዚህ ጉዳይ የሥር ፍ/ቤት በሥረ ነገሩ ላይ የመጨረሻ ፍርድ ባልሰጠበት ጉዳይ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ የማይችል ሆኖ ሳለ የክልል ሰበር ችሎት የመጨረሻ ዉሳኔ ያልተሰጠበትን ጉዳይ ተቀብሎ መወሰኑ፣ የክልል ሰበር ችሎት ማስረጃ ለመመወዘን ስልጣን ሳይኖረዉ ባልተሰጠዉ ስልጣን ማስረጃን በመመዘን ፍሬ ነገር በመመርመር ዉሳኔ የሰጠ በመሆኑ፣ አመልካች ያቀረበዉ የዳግም ዳኝነት ጥያቄ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.6 የሚያሟላ ሆኖ ሳለ የክልሉ ሰበር ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልን የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ እንዲጸናልን በማለት አመልክቷል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ዉሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ይህ ሰበር ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.6 መሰረት ያቀረበዉን የዳግም ዳኝነት ይታይልኝ ጥያቄ የሀላባ ቁሊቶ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከተቀበለ በኋላ በሥረ-ነገር ጉዳይ ላይ አከራክሮ ዉሳኔ ባልሰጠበት ሁኔታ ተጠሪ ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ተቀብሎና አከራክሮ የዳግም ዳኝነት መስፈርትን የማያሟላ ነዉ በማለት የሥር ፍ/ቤትን ብይን መሻሩ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.6፣ 320 እንዲሁም ይህ ሰበር ችሎት በሰ.መ.ቁ.116209 ከሰጠዉ ገዥ ትርጉም አንጻር መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን፣ ለማጣራት ሲባል የሰበር አቤቱታዉ በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ባዘዘዉ መሰረት በ10/8/2016 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል። የመልሱም ይዘት ባጭሩ፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.6 መሰረት የቀረበዉን የዳግም ዳኝነት ጥያቄ በተመለከተ ዳኝነቱ እንዲገና ሊታይ ይገባዋል ወይም አይገባዉም በማለት በተሰጠዉ ዉሳኔ ላይ ይግባኝ ማቅረብ ባይቻልም መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት እንደሆነ ለሚመለከተዉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቅሬታ ማቅረብ እንደሚቻል ነዉ፤ በዚህ መሰረት ተጠሪ የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔን በተመለከተ አቤቱታዉን ለክልሉ ሰበር ችሎት ማቅረቡ ተገቢ ነዉ፣ ችሎቱም ጉዳዩን ተቀብሎ አይቶ የአመልካች አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 6 ሥር የተመለከተዉን የዳግም ዳኝነት ጥያቄ መስፈርት የሚያሟላ አለመሆኑን በመገንዘብ የሰጠዉ ዉሳኔ የሚነቀርበት የህ አግባብ የለም በማለት ተከራክሯል። አመልካች ያቀረበዉ የመልስ መልስ ባለመኖሩ ታልፏል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር እና ለሰበር ቅሬታዉ መነሻ የሆነዉን የክልሉ ሰበር ችሎት ዉሳኔን አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል። እንደመረመርነዉ የአሁን አመልካች በሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.6 መሰረት ያቀረበዉ የዳግም ዳኝነት ይታይልን አቤቱታ በፍ/ቤት ተቀባይነት አግኝቶ ጉዳዩ በዳግም ዳኝነት ሊታይ ይገባል ተብሎ ብይን መስጠቱን ማየት ተችሏል። የአሁን ተጠሪ በዚህ ብይን ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታዉን ለክልሉ ሰበር ችሎት ያቀረበ ሲሆን ችሎቱ ጉዳዩን በማየት አመልካች የዳግም ዳኝነት ይታይልን አቤቱታዉ ጋር ያቀረበዉ ማስረጃ የለም፣ አቤቱታዉ የሕጉን መስፈርት አያሟላም በማለት መወሰኑን መዝገቡ ያሳያል።

እንደሚታወቀዉ በሕግ ስልጣን የተሰጠዉ ፍ/ቤት የመጨረሻ የፍርድ ዉሳኔ ከሰጠ በኋላ ቀድሞ በፍርድ የተወሰነዉ ክርክር ሥረ-ነገርና የተያዘዉ ጭብጥ አንድ ዓይነት ከሆነ በዚህ ጉዳይ ላይ ሁለተኛ ክስ ወይም ማናቸዉም ሌላ ክርክር ማቅረብ እንደማይቻል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.5 (1) ሥር ተመልክቷል። ነገር ግን በልዩ ሁኔታ ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.6 ሥር የተመለከቱትን መስፈርቶች የሚያሟላ እንደሆነ የመጨረሻ የፍርድ ዉሳኔ ያገኘ ጉዳይ ዳግም ዳኝነት እንዲታይ  ሥርዓት ጉዳዩ ድጋሚ እንዲታይ መጠየቅ እንደሚቻል ያመለክታል። በዚህ ድንጋጌ መሰረት የቀረበዉን የዳግም ዳኝነት ይታይልን አቤቱታ ፍ/ቤቱ መርምሮ ዳኝነቱ እንደገና ሊታይ ይገባል ወይም አይገባም በማለት የወሰነ እንደሆነ፣ በዚህ ጉዳይ ይግባኝ ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ማቅረብ እንደማይቻል በንዑስ አንቀጽ 4 ሥር ተደንግጎ እናገኛለን። በዚህ መሰረት ዳኝነቱ እንደገና ሊታይ አይገባም ተብሎ የተወሰነ እንደሆነ አቤቱታ አቅራቢዉ ይግባኝ ማለት ባይችልም በዉሳኔዉ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የሚል እንደሆነ የሰበር አቤቱታዉን ለሚመለከተዉ ሰበር ችሎት ማቅረብ ይቻላል። ምክንያቱም ዳኝነቱ እንደገና ሊታይ አይገባም ተብሎ የተሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.320 (1) መሰረት የመጨረሻ ዉሳኔ እንደመሆኑ መጠን አቤቱታ አቅራቢዉ በዚህ ዉሳኔ ቅሬታ ያለዉ እንደሆነ ለሰበር

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ችሎት እንኳን ማቅረብ ካልቻለ በኢፌዴሪ ሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37 ሥር የተረጋገጠዉን ፍትሕ የማግኘት ሕገ መንግስታዊ መብቱን ስለሚነፍግ፣ ቅሬታ ካለዉ ለሚመለከተዉ ሰበር ችሎት ማቅረብ ይቻላል።

በሌላ በኩል ግን ዳኝነቱ ድጋሚ ሊታይ ይገባል ተብሎ የተወሰነ እንደሆነ፣ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 6 (4) መሰረት በዚህ ዉሳኔ ላይ ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኝ ማቅረብ እንደማይቻል የተደነገገዉ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.320 (1) እና (2) ድንጋጌ አንጻር ሲታይ ዳኝነቱ እንደገና ሊታይ ይገባል ተብሎ የተሰጠዉ ዉሳኔ ገና በዋናዉ ጉዳይ ላይ ክርክሩ የሚቀጥል በመሆኑ፣ ይግባኝ የሚባልበት የመጨረሻ ዉሳኔ ነዉ ለማለት ስለማይቻል ነዉ፤ ከዚህም በላይ በዋናዉ ጉዳይ ላይ ዉሳኔ ከተሰጠ በኋላ በዉሳኔዉ ቅሬታ ያደረበት ወገን በዋናዉ ጉዳይ ላይ በተሰጠዉ ዉሳኔ ላይ ካለዉ ቅሬታ ጋር አካትቶ መጀመሪያዉኑ ዳኝነቱ እንደገና ሊታይ ይገባል ተብሎ መፈቀድ አልነበረበትም የሚለዉን ቅሬታዉን ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት እና ለሚመለከተዉ ሰበር ችሎት ከማቅረብ የሚከለክለዉ ነገር ባለመኖሩ ነዉ። ስለሆነም ዳኝነቱ እንደገና ሊታይ ይገባል ተብሎ የተወሰነ እንደሆነ የመጨረሻ ዉሳኔ ባለመሆኑ እና በዋናዉ ጉዳይ ላይ ዉሳኔ ከተሰጠ በኋላ በዉሳኔዉ ላይ ካለዉ ቅሬታ ጋር ዳኝነቱ ድጋሚ ሊታይ ይገባል ተብሎ መፈቀድ አይገባም የሚል ወገን በዚህም ላይ ቅሬታዉን ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤትም ሆነ ለሚመለከተዉ ሰበር ችሎት ማቅረብ ስለሚችል ገና በዋናዉ ጉዳይ ላይ ዉሳኔ ሳይሰጥ ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤትም ሆነ ለሰበር ችሎት ቅሬታ ሊቀርብ አይገባም መባሉ ተገቢ ነዉ።

በሌላ በኩል ዳኝነቱ እንደገና ሊታይ አይገባም ተብሎ የተወሰነ እንደሆነ እና በዋናዉ ጉዳይ ላይ በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ ቅሬታ ያለዉ ወገን ይግባኝ ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ያቀረበ እንደሆነ እና ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ የሥር ፍ/ቤት ከጅምሩም ዳኝነቱ እንደገና ሊታይ ይገባል ብሎ መፍቀዱ ተገቢ አይደለም፣ ዳኝነት ድጋሚ ሊታይ አይገባም በማለት የሥር ፍ/ቤት የዳግም ዳኝነት ሊታይ ይገባም በማለት የወሰነዉን እና በዋናዉ ጉዳይ ላይ የሰጠዉን ዉሳኔ ጭምር በመሻር የወሰነ እንደሆነ፣ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.6 (4) መሰረት ከዚህ ዉሳኔ ላይ ይግባኝ ማለት ስለማይቻል፤ ቅሬታ ያለዉ ወገን ቅሬታዉን ማቅረብ ያለበት ስልጣን ላለዉ ሰበር ችሎት መሆን እንዳለበት መገንዘብ ያስፈልጋል።

በዚህ አግባብ አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የሀላባ ቁልቶ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.6 መሰረት ያቀረበዉን የዳግም ዳኝነት ይታይልን አቤቱታ መርምሮ በሰጠዉ ዉሳኔ የተጠሪን አቤቱታ በመቀበል ዳኝነቱ እንደገና ሊታይ ይገባል በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ፣ በዋናዉ ጉዳይ ላይ ክርክሩ የሚቀጥል በመሆኑ ዉሳኔዉ የመጨረሻ ዉሳኔ ነዉ ለማለት ስለማይቻል፣ በዋናዉ ጉዳይ ላይ ዉሳኔ ከተሰጠ በኋላ አመልካች በዚህ ዉሳኔ ላይ ቅሬታ ያለዉ እንደሆነ፣ ዳኝነቱ ድጋሚ ሊታይ ይገባል ተብሎ መወሰን አይገባም ነበር የሚል ቅሬታም ካለዉ፣ ቅሬታዉን ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤትም ሆነ ሂደቱን ጠብቆ ለሚመለከተዉ ሰበር ችሎት ማቅረብ እየቻሉ፣ ዋናዉ ጉዳይ ታይቶ ዉሳኔ ባልተሰጠበት ሁኔታ ለክልሉ ሰበር ችሎት ቅሬታ ማቅረቡ እና የክልሉ ሰበር ችሎት ከፍ ሲል በተጠቀሰዉ ምክንያት ቅሬታዉን ዉድቅ ማድረግ ሲገባዉ በመቀበል ደኝነቱ ድጋሚ ሊታይ አይገባም በማለት የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በመሻር ያሳለፈዉ ዉሳኔ የህግ ድጋፍ የለዉም። ከዚህ አንጻር የክልሉ ሰበር ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ ይህ ሰበር ችሎት በሰ.መ.ቁ.116209 ላይ ከሰጠዉ አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሚቃረን ሆኖ እናገኛለን። የክልሉ ሰበር ችሎት ዳኝነቱ እንደገና እንዲታይ በተሰጠዉ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ዉሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ብይን ላይ ተጠሪ ያቀረበዉን አቤቱታ ተቀብሎ ማስተናገድ አልነበረበትም፣ ችሎቱ አቤቱታዉን ዉድቅ በማድረግ ተጠሪ በዋናዉ ጉዳይ ላይ ዉሳኔ ሲሰጥ ቅሬታ ያለዉ እንደሆነ የዳግም ዳኝነት ይታይ ብይን ላይ ያለዉን ቅሬታ ጨምሮ ማቅረብ እንደሚችል በመጠቆም አቤቱታዉን ዉድቅ ማድረግ ይገባዉ ነበር። ይህ ሰበር ችሎት በኢፌዴሪ ሕገ መንግስት እና በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2 (4) (ሸ) እና 10 (1) (ሐ) መሰረት ከሰጠዉ ስልጣን አንጻር አመልካች ያቀረበዉ ቅሬታ የክልሉ ሰበር ችሎት በዚህ ጉዳይ የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን ስለሚያመለክት ቅሬታዉ ተቀባይነት የለዉ ነዉ ብለናል።

ሲጠቃለል የክልሉ ሰበር ችሎት የሥር ፍ/ቤት አመልካች ያቀረበዉን የዳግም ዳኝነት ይታይልን አቤቱታ ተቀብሎ ዳኝነቱ እንደገና እንዲታይ በማለት በሰጠዉ ብይን ላይ በተጠሪ የቀረበዉን የሰበር አቤቱታ ዉድቅ ማድረግ ሲገባዉ አቤቱታዉን ተቀብሎ ግራ ቀኙን በማከራከር የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተከታዩ ተወስኗል።

**<u>ዉሳኔ</u>**

1. የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.78161 መጋቢት 07 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9 (1) መሰረት ተሽሯል።
2. የአሁን ተጠሪ የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በዋናዉ ጉዳይ ላይ የሚሰጠዉ ዉሳኔ መብቴን ነክቷል የሚል እንደሆነ በዚህ ዉሳኔ ላይ ከሚያቀርበዉ ቅሬታ ላይ በመጨመር ዳኝነቱ እንደገና ሊታይ ይገባል ተብሎ በተሰጠዉ ዉሳኔ ላይ ያለዉን ቅሬታ አካትቶ ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት እና ለክልሉ ሰበር ችሎት ማቅረብ ይችላል ብለናል።
3. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤት ይድረስ።
4. ግራ ቀኙ የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ።
5. ይህ ሰበር ችሎት ግንቦት 28 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠዉ የአፈጻጸም የእግድ ትዕዛዝ በዚህ ትዕዛዝ ተነስቷል። ይጻፍ።

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፍ/ደ

<u>ማስታወሻ</u>፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የሰ/መ/ቁ 246954

ጥቅምት 8 ቀን 2017 ዓ.ም

**ዳኞች** ፡-ሽመክት አሰፋ

ገበየሁ ፈለቀ

አለማየሁ ሹናራ

ተናኜ ጥላሁን

ዘውዲቱ ታደሰ

አመልካች፡-ወ/ሮ ቀለም ተሰማ - አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡-1. አቶ ገበየሁ ታደሰ | የሁለቱም ጠበቃ አቶ አገኘሁ መኮንን ቀረቡ

2. አቶ አረጋ ታደሰ | አቶ አረጋ ታደሰም ቀረበ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ሲሆን ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ግንቦት 09 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 0334749 በቀን 15/06/2015 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡ ጉዳዩ የይዞታ ክርክር ሲሆን የተጀመረው የአሁን ተጠሪዎች በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ደቡብ ወሎ መስ/ዞን የጃማ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር ተጠሪዎች ከሳሽ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በስር ፍ/ቤት ከሳሾች የሆኑት የአሁን ተጠሪዎች በውርስ ከአባታቸው ጋር በድልድል ያገኙት ይዞታ ላይ ያለ ባህርዛና ፍቤት ለአመልካች በአደራነት እንድትጠቀምበት ሰጥተዋት አላስረክብም ያለች በመሆኑ ቤቱንና ግምቱ 20,000 የሆነውን ባህርዛፍ እንድታስረክባቸው እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡

አመልካች የአመልካቾች ክስ ደርሷት ከመልሷ ጋር ባቀረበችው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ክሱ በይርጋ የታገደ ነው፤ የቦታው አዋሳኝ ስላልተጠቀሰና ክሱ ግልጽ ስላልሆነ ሊሻሻል ይገባል በማለት አቅርባለች፤ የፍሬ ጉዳይ ክርክርም አቅርባለች ፡፡ ፍ/ቤቱ ከሳሾች የይዞታውን አዋሳኝ ጠቅሰው ክሱን እንዲያሻሽሉ በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ተጠሪዎች አዋሳኙን ጠቅሰው ክሳቸውን አሻሽለው አቅርበዋል፡፡

በመቃወሚያው ላይ ክርክር ለመስማት በተቀጠረበት ቀጠሮ ከሳሾች በቀን 15/07/2013 ዓ.ም የተጻፈ የክስ ይሻሻል አቤቱታ አቅርበው ፍ/ቤቱም ከፈቀደላቸው በኋላ የተሸሻለውን ክስ ለመጠባበቅ በተቀጠረው ቀነ ቀጠሮ ፍ/ቤቱ መዝገቡ ሲመረመር አመልካቾች ክስ እንዲያሻሽሉ የተፈቀደላቸው ቢሆንም ቀደም ሲል ክስ ያሻሽሉ መባሉን ባለመገንዘብና ሌላ ዳኛ የፈቀደለት መሆኑን ሳይመረምር መፍቀዱ ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት ተገቢ ሆኖ ስላልተገኘ በቀን 15/07/2013 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 208 መሰረት በማረም ክሱ ሊሻሻል አይገባም በማለት ትዕዛዝ ሰጥቶ በመቃወሚያው ላይ ክርክሩን ከሰማ በኋላ የከሳሽ ክስ በ10 ዓመት ይርጋ ይታገዳል በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡

አመልካቾችም የህንን ብይን በመቃወም ለደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው በመ/ቁ 51420 በቀን 24/10/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት ፍ/ቤቱ መዝገቡን ከመረመረ በኋላ የስር ፍ/ቤት ክሱን አመልካቾች እንዲያሻሽሉ ከፈቀደ በኋላ ተገቢ አይደለም በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 208 መሰረት በማረም ክሱ ሊሻሻል አይገባም የማለቱን አግባብነት ከስነስርዓቱ ህጉ አኳያ፣ ክርክሩ በ10 ዓመት ይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት ብይን የመስጠቱን አግባብነት ለማጣራት ሲባል ያስቀርባል በማለት የስር ፍ/ቤት የሰጠው ትዕዛዝ በበላይ ፍ/ቤት ከሚሻር በቀር በድጋሚ ትእዛዙን በሰጠው ፍ/ቤት እንደ አጻጻፍ ስህተት ተቆጥሮ በራሱ በፍ/ቤቱ ትዕዛዙ መነሳቱ የስነስርዓት ህጉን የተከተለ አይደለም በማለት ሁለተኛውን ነጥብ ሳይረምር በማለፍ የስር ፍ/ቤት ተጠሪዎች አሻሽለው ያቀረቡትን ክስ በመቀበል በማከራከር በተሻሻለው ክስ ላይ መልስ እንዲቀርብ በማድረግ ክርክሩን በድጋሚ እንደአዲስ በመምራት በጉዳዩ ላይ ዳኝነት እንዲሰጥ ለስር ፍ/ቤት መልሶለታል፡፡

በከፍተኛው ፍ/ቤት ውሳኔና ለሥር ፍርድ ቤቱ ጉዳዩ በተመለሰበት ነጥብ መሰረት የስር ፍ/ቤቱ ተጠሪዎች የክሱ ይዘት ሳይቀየር ከተከሳሾች ውጪ የውርስ ይዞታቸውን የያዙባቸውን ሌሎች ሁለት ሰዎች በክሱ ውስጥ በማስገባት ክሳቸውን አሻሽለው እንዲቀርቡ ታዞ ለመጠባበቅ ተቀጥሮ ተጠሪዎች አንዱን ግለሰብ ብቻ አስገብተው የውርስ ንብረቱን የግላቸው አድርገው አቅርበዋል በማለት በቀን 21/11/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 91(1) መሰረት ክሳቸውን የማሻሻል መብታቸውን አልፎ በመቃወሚያ ላይ ክስ ለመስማት ቀጠሮ ተይዞ የነበረ ሲሆን፣ ክሱ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ሊሰማ በተያዘው ቀጠሮ ዕለት ተጠሪዎች ለመከራከር ፍቃደኛ አለመሆናቸውን በመግለጻቸው የሥር ፍርድ ቤቱ መዝገቡን ዘግቶ ወደ መ/ቤት መልሶታል፡፡

አመልካቾች ይህን የሥር ፍርድ ቤቱን ትዕዛዝ በመቃወም ለደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ውሳኔው ሳይለወጥ ቀርቷል፡፡

ተጠሪዎች በዚህ ውሳኔ ቀር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍ/ቤቱ በመ/ቁ 0334749 በቀን 15/06/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት በግራቀኙ የቀረቡትን ክርክሮች ከመረመረ በኋላ ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት በመጀመሪያ የስር ፍ/ቤቱ የሥረ-ነገር ስልጣን ያለው ስለመሆንና ያለመሆኑ መታየት አለበት በማለት 1ኛ ተጠሪ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ መሆኑን በቀረበው ክስ ላይ የተመለከተ ሲሆን ዳኝነት የተጠየቀበት ይዞታ በአማራ ክልል ደቡብ ወሎ ጃማ ወረዳ 07 ቀበሌ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ክርክሩን የሚጠይቁበት መንገድ ውርስ ወይም ውክልና ወይም አደራ የሚለው ከሚዛን ውስጥ ሳይገባ ለክርክር መነሻ የሆነው ይዞታ እንደመደበኛ የገጠር መሬት ክርክር የሚያስቆጥረው ስለሆነ ለክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሚቀርብ ሳይሆን በፌደራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 5(1) (ሸ) መሰረት ለፌደራል ፍ/ቤቶች ስልጣን ስር የሚወድቅ ነው፡፡ ስለሆነም የጃማ ወረዳ ፍ/ቤት በተጠሪዎች የቀረበውን የዳኝነት ጥያቄ ለመስጠት የሚያስችል የስረ ነገር ስልጣን የለውም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ግንቦት 9 ቀን 2015 ዓ/ም ጽፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይህን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ሲሆን ይዘቱም የክልል ፍ/ቤቶችን ለመቋቋምና ስልጣንና ተግባራቸውን ለመደንገግ የወጣው አዋጅ ቁጥር 281/2015 አንቀጽ 14(4) (ሀ) መሰረት የክልል ፍ/ቤቶች የክልል ህጎችን በተመለከተ ለመተርጎምና ለመዳኘት ስልጣን ያላቸው በመሆኑ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ያላቸው የክልሉ ፍ/ቤቶች ናቸው፤ በሌላ በኩል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 23 በውርስ ምክንያት ክርክር በተነሳበት ጊዜ ክሱ የሚቀርበው የውርሱ ክፍያ በተጀመረበት ቦታ ለሚያስችለው ፍ/ቤት እንደሆነ ደንግጎ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የስር ወረዳ ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ አከራክሮ ለመወሰን የሚያስችል ስልጣን የለውም መባሉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ መታረም የሚገባው ነው፡፡

ክርክሩን የስር ከሳሾች የአሁን ተጠሪዎች ጀምረውት ሳለ እና የስሥር አመልካችም መቃወሚያ ባላቀረብኩበት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በተከራካሪ ወገኖች ያልተነሳ ጉዳይ በማንሳት የተጠሪዎች አድራሻ በአማራ ክልል ሆኖ እያለ የአንደኛው ተከራካሪ አድራሻ አዲስ አበባ ነው በሚል ምክንያት የፌ/ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 5(1) (ሸ) ን በመጥቀስ የወረዳው ፍ/ቤት ስልጣን የለውም በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ክርክር ያስነሳው ቤትና ባህርዛፍ ያረፈበት መሬት የገጠር መሬት ነው? ወይስ በከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ ነው? የሚለው ሳይለይ፣ የተከራካሪ ወገኖችን የተለያየ ክልል ነዋሪዎች መሆናቸውን ብቻ መሰረት በማድረግ ጉዳዩን የማየት ስልጣን ያላቸው

በአዋጅ ቁጥር 1234/2013፤ አንቀጽ 5/91/ሸ መሰረት የፌደራል ፍ/ቤቶች ናቸው በማለት ደቡብ ወሎ ዞን የጃማ ወረዳ ፍ/ቤት ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የለውም በሚል የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የመወሰኑን አግባብነት ከክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 133/1998 አንቀጽ 29 እና በደንብ ቁጥር 51/1999 አንቀጽ 35 (4) እንዲሁም ሰበር ችሎቱ አዋጅ ቁጥር 133/1999 አንቀጽ 29 እና በደንብ ቁትር 51/1999 አንቀጽ 35(4) እንዲሁም ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ 106560፣ 116583፣ 138445፣ 131777 እና በሌሎች መሰል መዝገቦች ላይ ከተሰጠው ገዢ ውሳኔዎች አንጻር ለመመርመር ሲባል ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪዎች ሰኔ 17ቀን 2016 ዓ.ም በተጻፈ የሰጡት መልስ ይዘት ባጭሩ የአከራካሪው ይዞታ የባለቤትነት ደብተር ላይ የመሬቱ አጠቃቀም የመኖሪያ አካባቢ የሚል በመሆኑ ይዞታው ለ26 ዓመት ተጠሪዎች ይዘን በውርስ ከወላጆቻችን የተላለፈልንና የተከልናቸው ዛፎች ያሉበት መኖሪያ እንጂ የእርሻ መሬት አይደለም፡፡ የአማራ ክልል አዋጅ ቁጥር 133/1998 እና ደንብ ቁጥር 51/1999 ተሽሯል፤ በስራ ላይ ያሉት አዋጅ ቁጥር 252/2009 እና ደንብ ቁጥር 159/2010 የሚያነሷቸው ጭብጦች ከአካባቢ ባህል አንጻር አለመግባባቶችን በሽምግልና ከመቋጨት አንጻር የተደነገጉ በመሆናቸው ከአመልካች ጋር በሽምግልና ለመስማማት ፈቃደኛ ሆነን አመልካች ለመስማማት ባለመፍቀዷ ክርክሩ ወደ መደበኛ ፍ/ቤት ሄደናል፡፡ ስለሆነም በአዋጁ መሰረት በሽምግልና ለመስማማት ተሞክሮ ወደ መደበኛ ፍ/ቤት መቀጠሉ በአግባቡ ነው፡፡

በአዋጅ ቁጥር 1234 አንቀጽ 5/1/ሸ የተከራካሪዎችን የመኖሪያ ክልል የተለያየ መሆን ከግዛት ክልል የዳኝነት ስልጣን አንጻር ደነገገ እንጂ የተከራካሪዎችን የክርክር ጭብጥ ልዩነት አላደረገም፡፡ ስለዚህ ተከራካሪዎቹ በተለያዩ ክልሎች ውስጥ የምንኖር መሆኑን ጠቅሶ የክልሉ ሰበር የወረዳው ፍ/ቤት ስልጣን የለውም በማለት የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍበት ህጋዊ ምክንያት ስለሌለ አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ውድቅ ተደርጎ በህግ ስልጣኑ በተሰጠው በደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩ በህግና በማስረጃ ተመርምሮ በተያዘበትና በተጀመረበት ሁኔታ ጉዳያችን ውሳኔ እንዲሰጥልን፤ በክርክሩ ምክንያት ለደረሰብን መጉላላት ወጪና ኪሳራ ይከፈለን በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ግራቀኙ ክርክርና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፣ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ህጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ የቻልነው ፍሬ ጉዳዩን በማስረጃ የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው የክልሉ ወረዳ ፍርድ ቤት በተጠሪዎች የቀረበውን ክስ ተመልክቶ አመልካችም መልስ እንዲሰጡበት አድርጎ ካከራከረ በኋላ የሰጠው ብይን የይግባኝ ቅሬታ ቀርቦበት በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተሽሮ ጉዳዩ ከተመለሰለት በኋላ የወረዳው ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ክስ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የማሻሻል መብታቸውን በማለፍ ትዕዛዝ ከሰጠ በኋላ፣ ክሱን ሊሰማ ፍርድ ቤቱ በያዘው ቀጠሮ ተጠሪዎቹ ክሳችንን ማሻሻል ካልተፈቀደልን ለመከራር ፈቃደኛ አይደለንም በማለታቸው ፍርድ ቤቱ መዝገቡን ሲዘጋው፣ ተጠሪዎች ይግባኝ አቅርበው የሥር ፍርድ ቤቱ ብይንና ትዕዛዝ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ሳይለወጥ የቀረ ሲሆን፣  ተጠሪዎች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ መነሻነት  ተከራካሪዎቹ የአማራ ክልል እና የአዲስ አበባ ነዋሪዎች በመሆናቸው የሥር ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት የሥረ ነገር ስልጣን የለውም በማለት ነው የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ የሻረው፡፡

በመሠረቱ የሥር ፍርድ ቤቱ ወደ ፍሬ ጉዳዩ ገብቶ የሰጠው ውሳኔ የሌለ ቢሆንም የሥር ከሳሾች የሆኑት የአሁን ተጠሪዎች ክሱን በተፈቀደላቸው ጊዜ አሻሽለው ባለመቅረባቸው ምክንያት ፍርድ ቤቱ የማሻሻል መብታቸውን በማለፉ፣ ክስ የማሻሻል መብታችን ከታፈብን ክርክሩን አንቀጥልም በማለታቸው ፍርድ ቤቱ መዝገቡን በመዝጋቱ ነው የተጠሪዎቹ የይግባኝ ቅሬታ ምክንያት፡፡ በመሆኑም ወደ ፍሬ ጉዳዩ ተገብቶ የግራ ቀኙ ክርክር ያልተሰማና አከራካሪው ጭብጥ ያልተለየ በመሆኑ አከራካሪው ይዞታ የገጠር መሬት ነው አይደለም በሚለው ላይ ፍርድ ቤቱ ውሳኔን አላሳረፈበትም፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 138445 ከገጠር መሬት ጋር ተያይዘው የሚነሱ አለመግባባቶች እና ክርክሮች በስምምነትና በሽምግልና መፈታት ካልቻሉ ክልሎች በሚያወጡት ህግ መሠረት ውሳኔ እንዲያገኙ በአዋጅ ቁጥር 456/1997 መደንገጉንና የተከራካሪ ወገኖች መደበኛ መኖሪያ ቦታ ከግምት ሳይገባ ከእርሻ መሬት ጋር ተያይዘው የሚነሱ ክርክሮች ካላቸው ልዩ ባህሪ አንጻር በክልል ህግ ሥልጣን በሚሰጣቸው ፍርድ ቤቶች ብቻ እንዲፈቱ በመወሰኑ ከገጠር የእርሻ መሬት ይዞታ ጋር ተያይዘው ክርክሮች በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን የማየት ስልጣን ያለው የገጠር እርሻ ይዞታው የሚገኝበት የመሬት የዳኝነት ኮሚቴ በመሆኑ ጉዳዩን የፌዴራል ጉዳይ አያደርገውም በማለት  አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሥር ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት የሥረ ነገር ስልጣን የለውም ለሚለው ድምዳሜው መነሻ ያደረገው የተከራካሪ ወገኞችን በተለያየ ክልል መኖር መነሻ በማድረግ ብቻ ሲሆን፣ ከዛ አስቀድሞ ሊጣራ የሚገባውን ክርክር ያስነሳውን ቤትና ባህር ዛፍ ያረፈበት መሬት የገጠር መሬት  ወይም በከተማ ይዞታ ውስጥ የሚገኝ ቤት ስለመሆኑ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ማረጋገጥ ሲሆን፣ ይዞታው የገጠር መሬት ወይም የከተማ መሬት መሆኑን ካረጋገጠ በኂላ ይዞታው የከተማ መሬት ሆኖ ከተገኘ የሥረ ነገር ስልጣንን አስመልክቶ በህጉ መሠረት ተገቢ የሚለውን ብይን ሊሰጥበት ሲገባ፤ ይህንን ሳያጣራና ሳያረጋግጥ የተከራካሪዎቹን በተለያየ ክልል መኖርን ብቻ መነሻ በማድረግ የሥር ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት የሥረ ነገር ስልጣን የለውም ሲል የደረሰበት ድምዳሜ አግባብነትን ተገቢውን የክርክር አመራር ያልተከተለ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 0334749 በቀን 15/06/2015 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 ተሽሯል ፡፡
2. ክርክር ያስነሳውን ቤትና ባህር ዛፍ ያረፈበት መሬት የገጠር የእርሻ መሬት ወይም በከተማ ይዞታ ውስጥ የሚገኝ ቤት ስለመሆን አለመሆኑ በተገቢው አካል እንዲጣራ በማድረግ ይዞታው የገጠር መሬት ወይም የከተማ መሬት መሆኑን ከለየ በኂላ ይዞታው የከተማ ይዞታ ሆኖ ከተገኘ የሥረ ነገር ስልጣንን አስመልክቶ በህጉ መሠረት ተገቢ የሚለውን ብይን እንዲሰጥበት፣

   ይዞታው የገጠር የእርሻ መሬት ሆኖ ከተገኘም በአዋጅ ቁጥር 456/1997 እንዲሁም በክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ መሠረት ክሱ የቀረበለት የክልሉ ደቡብ ወሎ ዞን የጃማ ወረዳ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ሥልጣን ያለው ስለሚሆን በሥር ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ እና የደቡብ ወሎ መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት በሰጠው ፍርድ ላይ የቀረበውን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 343/1 መሠረት ጉዳዩን ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተመልሶለታል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ::

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

<u>ማስታወሻ</u>፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 246989

ጥቅምት 6 ቀን 2017 ዓ.ም

**ዳኞች** ፡-ሽመክት አሰፋ

ገበየሁ ፈለቀ

አለማየሁ ሹናራ

ተናኜ ጥላሁን

ዘውዲቱ ታደሰ

አመልካቾች፡- 1.ፋጡማ በከር
2.ሰቢዳ አብደላ } አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡- 1. ኑረዲን እስማኤል
2. ፈንዲ እስማኤል } አልቀረቡም

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ሲሆን ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች ግንቦት 9 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 422658 በቀን 24/08/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍ/ቤት ውሳኔዎችን በመሻር የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸው በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው መነሻነት ነው፡፡ ጉዳዩ የንብረት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በምስራቅ ሀረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የጉርሱም ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ በወረዳው ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር አመልካቾች ከሳሽ እንዲሁም ተጠሪዎች ተከሳሽ ነበሩ፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አመልካቾች ያቀረቡት ክስ ይዘት 1ኛ አመልካች የአባቴ የበከር ወዳይ የሆነ በጉርሱም ወረዳ ሺሮታ ቀበሌ እና በሙሳ ቀበሌ ውስጥ የሚገኘውን ይዞታ በ2008 ዓ.ም ለተከሳሾች አከራቼ ለ6 ዓመታት ይዘውት ሊለቁልኝ ፍቃደኛ አልሆኑም፡፡ 2ኛ አመልካች የአባቴ አቶ አብዱላ ሳሊ የሆነ በጉርሱም ወረዳ ከፍተኛ ሙሳ ቀበሌ ውስጥ የሚገኝ ስድስት ቦታዎች ተጠሪዎች ባለቤቴ ከሌላ ሚስት የወለዳቸው ልጆች ሲሆኑ ልጄ ታማሚ ስለሆነ እንወርሳለን በሚል ይዘውብኛል፡፡ ስለሆነም ተጠሪዎች የአመልቾችን ይዞታ ለቀው እንዲያስረክቡ ይወሰንልን በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

ተጠሪዎች በሰጡት መልስ ላይ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበው፣ ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ የሰጡት መልስ ይዘት 1ኛ ከሳሽ በኪራይ ለተጠሪዎች የሰጠችው መሬት የላትም፣ እየጠየቀች ያለችው አባታችን ለእኛ ለልጆቹ የተወውን ይዞታ ነው፡፡ ክርክር ያስነሳው መሬት የአባታችን እንጂ የ1ኛ ከሳሽ አባት ስላልሆነ ክሱ ውድቅ ይደረግ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍሬ ጉዳዩን በማስረጃ የማጣራትና የመመዘን ስልጣን ያለው የስር ፍ/ቤት የቀረበለትን የሰነድ እና የሰው ማስረጃዎች፣ የግራቀኙን የጽሁፍና የቃል ክርክር ሰምቶ የተከሳሽን የመጀመሪያ ደረጃ በብይን ውድቅ ካደረገ በኋላ፣ በፍሬ ጉዳይ ላይ ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት ተገቢነት ያላቸውን ጭብጦች ለይቶ ከያዘ በኋላ የግራቀኙን ምስክሮች ሰምቶ፣ በግራቀኙ የቀረቡትን የሰነድ ማስረጃዎች ከመረመረ በኋላ 1ኛ አመልካችን በተመለከተ ከመሬት ጽ/ቤት በቀረበው ሪፖርት ውጤት ክርክር ያስነሳው መሬት ግብር ስለመከፈሉ የሚገልጽ ነገር የሌለ ስለመሆኑና ተከራካሪዎቹ ቤተሰብ እንደሆኑና ክፍፍል እንዳላቸው ገልጸዋል፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ የተጠሪዎች አባት ሳይሆን 1ኛ አምካች ከአባቷ ያገኘችው ይዞታ እንደሆነ ፣ መሬቱም የአባቷ እንደሆነ እና ተከሳሾች በእኩሌታ ሊሰሩበት ከእርሷ ወስደው እነደነበር ብልጫ ባለው መልኩ በምስክሮች አስረድታለች በማለት፣ እንዲሁም የተከሳሾች አባት የ1ኛ ከሳሽ እናት ከሞተች በኋላ ካገባቸው የእንጀራ አባታቸው የተወለዱ ስለሆነ ይህንን መሬት መውረስም ሆነ እንደግል ይዞታቸው የመጠየቅ ህጋዊ መብት የላቸውም ሁለቱም ተጠሪዎች ለ1ኛ አመልካች እንዲለቁላት ፡፡ 2ኛ አመልካችን በተመለከተ ባዶ የቤት መሬት ፣ የኦዳ መሬት ፣ የሀሰን እና ወንዝ መሬት ይዞታዎች በሁለቱ አመልካቾች እጅ የሚገኙ እንዲሁም 2ኛ ከሳሽ ከቤተሰቦቿ የወረሰችው እና ያገኘችውን ይዞታ ወደ ተጠሪዎች አባት ወስዳ ከተጠሪዎች አባት ጋር የተጋባች መሆኑን ስላረጋገጠች፣ ተጠሪዎች ከአባታቸው እንደወረሱ ቢከራክሩም አባታቸው በአዋጅ ቁጥር 130/99 አንቀጽ 9/1 ፣2/16 እና አንቀጽ 226/2 የሌለውን መብት ለአመልካቾች ሊያወርስ ስለማይችል የ2ኛ አመልካች የሆነውን መሬት እነንዲለቁላት እንዲሁም የቡና በዲስዲማ የሚገኝና ሀጂ ይዞታዎች 2ኛ አመልካች ከባሏ ያገኘችው መሆኑ ስለተረጋገጠ ሁለቱ ተጠሪዎች እንዲለቁላት በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪዎች የህንን ውሳኔ በመቃወም ለምስራቅ ሀረርጌ ከፍተኛ ፍ/ቤት እና ለምስራቅ ሐረርጌ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የይግባኝ አቤቱታውን አቅርበው ውሳኔው ሳይለወጥ ቀርቷል፡፡

በመቀጠል ተጠሪዎች ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር ቅሬታቸውን አቅርበው ፍ/ቤቱ የግራቀኙን ክርክር ከስር ፍ/ቤት መዝገብ ገልባጭ እና አግባብነት ካላቸው ህጎች ጋር ከመረመረ በኋላ 1ኛ አመልካች ከአባቷ በውርስ ያገኘችውን ይዞታ በኮንትራት ውል ለአመልካቾች በ2008 ዓ.ም ውስጥ መስጠቷ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ስላልተረጋገጠ፣ አከራካሪው ይዞታ በውርስ ከአባቴ የተላለፈልኝ ነው በማለት በአሁን በተጠሪዎች ላይ ያቀረበችው ክስ ተቀባይነት የለውም ካለ በኋላ፣ 2ኛ አመልካችዋን በተመለከተ ከአባቷ በውርስ ያገኘችው ብቻ ሳይሆን ከአመልካቾች አባት ጋር በትዳራቸው ውስጥ አፍርተው በጋራ ሲጠቀሙበት የቆዩ መሆኑ ስለተረጋገጠ አከራካሪው ይዞታ ለሁለት ተካፍሎ የሚስትነት ድርሻዋ እንዲሰጣትና ቀሪው ግማሹ ደግሞ አመልካቾች የአባታቸው ወራሾች ስለሆኑ ሊለቁ አይገደዱም በማለት በሥር ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል ወስኗል።

አመልካቾች ግንቦት 9 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይህን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ሲሆን ይዘቱም 1ኛ አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት ከአባቴ በውርስ ያገኘሁት አመልካቾችም በኪራይ የይዞታውን እኩሌታ ይዘው እያረሱ ይጠቀሙበት እንደነበር የግራቀኙ ምስክሮች አስረድተው ባለበት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በ1ኛ አመልካች እና በተጠሪዎች መካከል በመሬት አስተዳደር ተረጋግጦ የተመዘገበ የመሬት ኪራይ ውል ስለሌለ ህጋዊ ባልሆነ ውል ላይ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ መስጠቱ ተገቢነት የለውም በሚል መሻሩ መሰረታዊ ህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው። 1ኛ አመልካች የጠየቀችው የአባቷን የውርስ ሀብት በመሆኑ መታየት የነበረበት ጭብጥ በዚህ መሬት የመጠቀም መብት የማን ነው? የሚል ሆኖ ሳለ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት የኪራይ ውልን እንደጭብጥ በመያዝ በስር ፍ/ቤት የተሰጡ ውሳኔዎችን መሻሩ መሰረታዊ ህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው።

2ኛ አመልካች ተጠሪዎች ላይ ክስ የመሰረተችበት መሬት የተጠሪዎችን አባት ከማግባቷ በፊት ከቤተሰቦቿ በውርስ ያገኘች መሆኑ ተረጋግጦ ባለበት ሁኔታ የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የ2ኛ አመልካች ይዞታ የባልና ሚስት ስለሆነ ተጠሪዎች የአባታቸውን ድርሻ ማግኘት አለባቸው በማለት የደረሰበት ድምዳሜ መሰረታዊ ህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው። የቀረቡት ምስክሮች 2ኛ አመልካች በክሱ ጠየቀችውን ይዞታ በመያዝ የተጠሪዎችን አባት አግብታ አብረው ሲጠቀሙበት የነበረ መሬት እንጂ የተጠሪዎች አባት አለመሆኑን አስረድተው በተጨማሪም የተጠሪዎች አባት ከተጠሪዎች እናት ጋር ያፈራውን የመሬት ይዞታ ያላቸው በመሆኑ ተጠሪዎች በአንድ በኩል አባታቸው ከእናታቸው ያፈራውን መሬት ይዞ በሌላ በኩል ደግሞ የእነሱ አባት 2ኛ አመልካችን ስላገባ ብቻ የተጠሪ አባት ወደዚህ ቤተሰብ ከመምጣቱ በፊት የነበረ መሬት የባልና ሚስት ይዞታ በማድረግ ተጠሪዎች የአባታቸውን ድርሻ የመውረስ መብት አላቸው በማለት የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔን እንዲያጸናልን በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው።

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የስር ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ አመልካቾች በክሳቸው የጠቀሱትን ፍሬ ነገር በማስረጃ አስረድተዋል በማለት የአሁን ተጠሪዎች ለክርክር መነሻ የሆነውን ይዞታ ለአመልካቾች እንዲለቁ የወሰኑ በመሆኑ የክልሉ ሰበር ችሎት በህግ ከተሰጠው ስልጣን አንጻር በስር ፍ/ቤት የቀረበው ማስረጃ ውሳኔ ለመስጠት በቂ አይደለም የሚል ከሆነ ወደ ስር ፍ/ቤት ተመልሶ ተጨማሪ ማስረጃ ቀርቦ እንዲጣራ ከሚያደርግ በቀር ማስረጃ መርምሮ ከሥር ፍ/ቤት የተለየ የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ በመድረስ፣ ተጠሪዎች ይዞታውን ሊለቁ አይገባም በማለት ያሳለፈው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 22603፣44804፣55273 (የታተሙ) ከሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም ውሳኔዎች አንጻር ለመመርመር ሲባል ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪዎች ሰኔ 04 ቀን 2016 ዓ.ም በተጻፈ የሰጡት መልስ ይዘቱ 2ኛ አመልካች አባታችንን አግብታ ከ 60 ዓመት በትዳር የቆየች ለክርክር ምክንያት የሆነው ይዞታ በትዳር ውስጥ ከአባታችን ጋር ያፈሩት ሲሆን አባታችን በህይወት እያለ የዛሬ 27 ዓመት ተጠሪዎችን ሲድሩ በስጦታ የሰጡን ነው፤ የስር ፍ/ቤት ይዞታው የ1 አመልካች የውርስ ሀብት ነው በማለት የደረሰበት መደምደሚያ ተገቢነት የለውም፤ 1ኛ አመልካች ያቀረበችው ክስ ምክንያት የሆነው የኪራይ ውል ዋጋ የሌለው ስለሆነና በዚህ ላይ ተመስርቶ የቀረበ ክስ አስገዳጅ ስላልሆነ ተጠሪዎች ይህንን ይዞታ ለመልቀቅ አይገደዱም የተባለበት እና 2ኛ አመልካች የጠየቀችው የመሬት ይዞታ የተጠሪዎች አባት እና 2ኛ አመልካች በትዳር ውስጥ ያፈሩት የጋራ ንብረት መሆኑን ተረጋግጦ ተጠሪዎች የአባታቸውን ድርሻ ይውረሱ ተብለው የተወሰነው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስላልሆነ ሊጸና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፤

አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ግራቀኙ ክርክርና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፣ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ህጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ የቻልነው ፍሬ ጉዳዩን በማስረጃ የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው የስር ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ የተጠሪዎች አባት ሳይሆን 1ኛ አምካች ከአባቷ ያገኘችው ይዞታ እንደሆነ እና የተጠሪዎች አባት የ1ኛ አመልካች እናት ከሞተች በኋላ ካገባቸው የእንጀራ አባታቸው የተወለዱ ስለሆነ ይህንን መሬት መውረስም ሆነ እንደግል ይዞታቸው የመጠየቅ ህጋዊ መብት የላቸውም በማለት ሁለቱም ተጠሪዎች ለ1ኛ አመልካች እንዲለቁላት በማለት እንዲሁም 2ኛ አመልካችን በተመለከተ ተጠሪዎች ከአባታቸው እንደወረሱ ቢከራከሩም አባታቸው በአዋጅ ቁጥር 130/99 አንቀጽ 9/1 ፣2/16 እና አንቀጽ 226/2 የሌለውን መብት ለአመልካቾች ሊያወርስ ስለማይችል የ2ኛ አመልካች የሆነውን መሬት እንዲለቁላት እንዲሁም የቡና በዲስዲማ የሚገኝና ሀጂ ይዞታዎች 2ኛ አመልካች ከባሏ ያገኘችው መሆኑ ስለተረጋገጠ ሁለቱ ተጠሪዎች እንዲለቁላት በማለት የሰጠው ውሳኔ፣ በክልሉ ከፍተኛና ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ያልተለወጠ ቢሆንም፤ የክልሉ ሰበር ሰሚው ችሎት ከላይ በተመለከተው ምክንያት የሥር ፍርድ ቤቶቹን ውሳኔ ያሻሻለ ሲሆን ማሻሻሉ አግባብ ነው ወይ? የሚለውን እንደሚከተለው ተመልክተነዋል፡፡

አመልካቾች ይህ የሥር ፍርድ ቤቶቹ ውሳኔ የተሻሻለበትን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመቃወም ላቀረቡት አቤቱታ በዋቢነት በጠቀሱት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 55273 በሰጠው ውሳኔ የደቡብ ብ/ብ/ህ/ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ፍሬ ጉዳይ የማጣራት ተጨማሪ ምስክር መስማትና ተጨማሪ ማስረጃ በመቀበል ማስረጃን በመመዘንና በመመርመር ውሣኔ መስጠቱ በክልሉ ጉዳይ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በተሰጠ የመጨረሻ ውሣኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የህግ ስህተት ከማረም ስሌጣኑ ውጭ በመውጣት ውሣኔ የሰጠ መሆኑን የሚያሣይ ሲሆን፣ የሰበር ሥርዓት በመሠረታዊ ባህሪ ከይግባኝ ሥርዓት የተለየ ሆኖ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት በመዝገቡ ላይ ተጨማሪ ምስክሮችን በመስማትና ሌሎች ፍሬ ጉዳዮችን በማጣራት ማስረጃ በመመዘን የሰጠው ውሣኔ የአመልካቹን የመከላከያ ማስረጃ የማቅረብና የመስማት መብት የሚያጣብብ በመሆኑ ውሳኔው መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን ገልጾ የወሰነበት ነው። ከዚህ ለአመልካቾች ክርክር በዋቢነት ከተጠቀሰው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አስገዳጅ የህግ ትርጉም መረዳት እንደሚቻለው የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር ደረጃ ፍሬ ጉዳዩን በማጣራት ተጨማሪ ምስክር ሰምቶና ማስጃን መዝኖ ውሳኔ መስጠቱ የይግባኝ ሰሚነት ሚና በመሆኑ ከሰበር ችሎት ባህሪ አንጻር ተገቢነት የሌለለው በመሆኑ ውሳኔው መሠረታዊ የህግ ስህተት ስለመሆኑ በመግለጽ አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠበት ነው።

በተያዘው ጉዳይ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሥር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ያሻሻለው ወደ ፍሬ ጉዳዩ በመግባት ተጨማሪ ማስረጃን በመስማት ሳይሆን፤ 1ኛ አመልካች ከአባቷ በውርስ ያገኘችውን ይዞታ በኮንትራት ውል ለአመልካቾች በ2008 ዓ.ም ውስጥ መስጠቷ በሥር ፍርድ ቤት በማስረጃ ያልተረጋገጠ ስለነበረ አከራካሪው ይዞታ በውርስ ከአባቴ የተላለፈልኝ ነው በማለት በአሁን በተጠሪዎች ላይ ያቀረበችው ክስ ማስረጃ ያልቀረበበት መሆኑን ጠቅሶ የሥር ፍርድ ቤቱ የፈጸመውን የማስረጃ ምዘና ስህተት ያረመ በመሆኑና 2ኛ አመልካችዋን በተመለከተ ከአባቷ በውርስ ያገኘችው ብቻ ሳይሆን ከተጠሪዎች አባት ጋር በትዳራቸው ውስጥ አፍርተው በጋራ ሲጠቀሙበት የቆዩ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤት በተደረገ ክርክርና በቀረበ ማስረጃ ተረጋግጦ እያለ በዚህ አግባብ የቀረበውን ማስረጃ የሥር ፍርድ ቤቱ በአግባቡ ሳይመዝን በማለፍ በአከራካሪው ይዞታ ላይ ተጠሪዎቹ ያላቸውን መብት ሳያረጋግጥ መቅረቱ የማስረጃ ምዘና ስህተት በመሆኑ በሥር ፍርድ ቤት በቀረበው ማስረጃ 2ኛዋ አመልካች ያላትን ግማሽ የሚስትነት ድርሻ በማረጋገጥና ቀሪው ግማሽ ድርሻ ላይም ተጠሪዎቹ ባለመብት ስለሚሆኑ፣ አከራካሪው ይዞታ ለሁለት ተካፍሎ ለ2ኛ አመልካችዋ የሚስትነት ድርሻዋ እንዲሰጣትና ቀሪው ግማሹ ደግሞ ተጠሪዎች የአባታቸው ወራሾች ስለሆኑ ሊለቁ አይገደዱም በማለት ወስኖ፣ በአግባቡ ማስረጃ ሳይመዘን ተሰጥቶ የነበረውን የሥር ፍርድ ቤቶቹን ውሳኔ ማሻሻሉ፣ የማስረጃ ምዘና ስህተትን ማረም ከመሆኑ በቀር መሠረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ነው ብለናል። በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል።

## <u>ውሳኔ</u>

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 422658 በቀን 24/08/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ባለመሆኑ ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 ጸንቷል
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻቻሉ።
3. በመዝገቡ የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፣ ይጻፍ።
4. መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

<u>ማስታወሻ</u>፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፍ/ደ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 247062

ጥቅምት 06 ቀን 2017 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-**ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ሾመ ሽፈራው

ሠናይት አድነው

ሀፊዝ አባ ጀማል

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ራሔል ገብረመድህን ጠበቃ አዲስ ሳዲቅ

**ተጠሪ፡-** ኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትሕ ሚኒስቴር ዐ/ህግ ማርቆስ ግርማ

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ግንቦት 10 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 229016 በቀን 10/06/2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የሽያጭ ውልን የሚመለከት ሆኖ ክርክሩ የተጀመረው በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን በስር ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ እና ተጠሪ ተከሳሽ ሆነው ተከራክረዋል፡፡

አመልካች ሰኔ 22 ቀን 2013 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት ክስ ተጠሪ የኮሮና ወረርሽኝ መከላከያ ቁሳቁሶች ከጉዳዩ አንገብጋቢነት እና አጣዳፊ ከመሆኑ አንፃር ከፌደራል የመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በተላለፈለት መመሪያ መሰረት ከመደበኛ የግዥ ስርዓት ውጪ እንዲገዛ ተፈቅዶለት ከአመልካች

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ላይ ግምታቸው ብር 500,654.67(አምስት መቶ ሺህ ስድስት መቶ ሃምሳ አራት ብር ከ64/100) የሆኑ ቁሳቁሶችን አመልካች ከማስተዳድረው የሰም ፕላስቲክ በቀጥታ ግዥ ገዝቶ በቀን 23/10/2012 ዓ.ም ተረክቦኛል፡፡ ተጠሪ መረከቡንም የሚያሳይ የዕቃዎች ዓይነት ብዛት እና ዋጋቸውን የያዘ የዕቃ ገቢ ማድረጊያ ደረሰኝ ሰጥቶኛል፡፡ ተጠሪ ክፍያ እንዲከፍል ማስጠንቀቂያ ቢሰጠውም ክፍያ ሊከፍል ስላልቻለ የዕቃውን ዋጋ ከነወለዱ ብር 545,713.56( አምስት መቶ አርባ አምስት ሺህ ሰባት መቶ አስራ ሶስት ብር ከ92/100) እንዲከፍል እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ መስከረም 15 ቀን 2014 ዓ.ም በሰጡት መልስ በሃገራችን በተከሰተው የኮሮና ወረርሽኝ ምክንያት የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በአዋጅ ቁ.649/2001 አንቀጽ 16(5) መሰረት በልዩ ሁኔታ ለኮሮና መከላከያ የሚያስፈልጉ ዕቃዎች ግዥ ከመደበኛው የግዥ አሰራር ሂደት ውጪ እንዲፈጸም በቀን 29/07/2012 ዓ.ም ለሁሉም የፌደራል መ/ቤቶች መመሪያ አስተላልፏል፤ የመ/ቤቱ ኃላፊ በኤጀንሲው የወጣውን መመሪያ እንደ አማራጭ እንጂ አስገዳጅ ባለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀፅ 15(1) መሰረት በውስን ጨረታ ዕቃዎችን ለመግዛት አመልካችን ጨምሮ 7 ድርጅቶች ግዥው ላይ ተጋብዘው አመልካች በ24/07/2020 ዓ.ም ከድርጅታቸው በተጻፈ ፕሮፎርማ ከ12 ቱ ውስጥ 6 ዓይነት ዕቃዎችን ዋጋ በመግለጽ ለውድድር ፈርመው ያቀረቡ ሲሆን የተቋሙ የበላይ ኃላፊዎች ከአቅራቢዎች የቀረቡት ፕሮፎርማዎች ግዥ ዘዴ ከመመሪያ በላይ በመሆኑ ግዥው ቀሪ ሆኖ ጨረታ ወጥቶ እንዲፈጸም ውሳኔ የተሰጠ መሆኑን፤ አመልካች በውስን ጨረታ ግዥ ማሸነፋቸው በጽሁፍ ሳይገለጽላቸውና ውል ሳይዋዋሉ ንብረቶቹን ለተጠሪ ንብረት ክፍል ማስረከባቸው ህጋዊ አለመሆኑን፤ ንብረቱን ለኣግባብ በተረከቡት የተቋሙ ሰራተኛ ላይ የዲስፕሊን እርምጃ እንዲወሰድ በምርመራ ሂደት ላይ መሆኑን፤ አመልካች ያቀረቡት ሞዴል 19 የዕቃ ገቢ ደረሰኝ ዕቃው በምን ሁኔታ ገቢ እንደተደረገ የማይገልጽ መሆኑን፤ ተጠሪ የመንግስት ተቋም ስለሆነ የሚፈጽማቸው ማናቸውም ውል በጽሁፍ መደረግ ያለበት መሆኑን፤ የግዥ ሂደቱ እንዲጠናቀቅ ወይም ግዥው በኮሮና መመሪያ መሰረት እንዲፈፀም በበላይ አመራር የተሰጠ ትዕዛዝ በሌለበት እና በመካከላችን የግዥ ውል በሌለበት በአመልካች ጥያቄ መሰረት የምንከፍልበት የሕግ አግባብ የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የግራቀኙን ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ አመልካች ከተጠሪ ጋር በኮሮና ወረርሽኝ ምክንያት ከመመሪያ ውጪ ለበሽታው መከላከያ የሚያገለግል ቁሳቁሶችን ሽያጭ እና ግዥ በመካከላቸው መኖሩን የሚገልፅ በተጠሪ መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ የፀደቀ ግዥ መኖሩን አላስረዱም፤ንብረቱን በሞዴል 19 ገቢ ማድረጋቸው አመልካች እና ተጠሪ ግዥ ፈጽመዋል የሚያስብል ስላልሆነ ተጠሪ አመልካች የጠየቁትን ገንዘብ ሊከፍሉ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱ ይግባኙን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አመልካች ግንቦት 10 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይህን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ሲሆን ይዘቱም የስር ፍ/ቤት ከግራቀኙ ክርክር አንጻር ተገቢውን ጭብጥ ሳይዝ ውሳኔ የሰጠ መሆኑን፤የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ባወጣው መመሪያ ቁጥር መግኤ/ሀ.3/1/1289 በመመሪያው ገጽ 2 ላይ በግዥዎች ላይ ቁጥጥር እና ክትትል የማድረግ ኃላፊነት የመ/ቤቱ ኃላፊ ሆኖ እያለ አመልካች ግዥው በበላይ ኃላፊ መፈቀዱን አላስረዱም በማለት የስር ፍርድ ቤት የደረሰበት ድምዳሜ ስህተት መሆኑን፤ ተጠሪ የቀረቡት ቁሳቁሶች ግዥ ተሰርዞ በመደበኛ የግዥ አዋጅ መሰረት እንዲከናወን ተደርጓል ቢሉም ይህንን የሚያስረዳ ማስረጃ አለማቅረባቸውን፤ የስር ፍርድ ቤት በኮሮና ወረርሽኝ ምክንያት እቃዎች በመ/ቤቱ ሃላፊ ፈቃድ ብቻ እንዲገዛ የተፈቀደ መሆኑን እና እቃዎቹን በሞዴል 19 ለተጠሪ መ/ቤት አመልካች ማስረከባቸውን ተጠሪ ባልካዱበት በግራቀኙ መካከል የግዥ ውል እንደተደረገ አያስቆጥርም በማለት የሰጠው ውሳኔ ስህተት በመሆኑ ሊሻር ይገባዋል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ በሰበር ችሎት ተመርምሮ በኮሮና ወረርሽኝ ምክንያት በአስቸኳይ ሁኔታ ለበሽታው መከላከያ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች ግዥን አስመልክቶ የኢፌድሪ የመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በቁጥር መግኤ/ሀ.3/1/1289 በቀን 29/07/2012 ዓ.ም ባስተላለፈው የግዥ አፈፃፀም ስርዓት መሰረት በአመልካችና ተጠሪ መካከል ግዥ አልተደረገም መባሉ የግራቀኙን ክርክር መሰረት ያደረገ መሆን አለመሆኑን፤ አመልካች በመንግስት የዕቃ ወይም ንብረት ገቢ ማድረጊያ ደረሰኝ(ሞዴል 19) መሰረት የግዥ ንብረቱን አስረክበው ከተጠሪ መ/ቤት ሞዴል ተቀርጦ ከተሰጣቸውና ለግዥውም ደረሰኝ ከሰጡ በኃላ በተጠሪ መ/ቤት የበላይ ኃላፊ የፀደቀ ግዥ መኖሩን አመልካች አላስረዱም ተብሎ መወሰኑ ህጉን የተከተለ መሆን አለመሆኑን፤ እንዲሁም በተጠሪ የበላይ ኃላፊ የፀደቀ ግዥ መኖሩን አመልካች አላስረዱም ቢባል እንኳን ተጠሪ ንብረቱን በሞዴል 19 መረከቡ ያላከራከረ ከመሆኑ አንጻር ግንኙነታቸው ቀሪ ሲሆን በተቻለ መጠን ግራቀኙ ወገኖች ስምምነት ከመደረጉ በፊት ወደነበሩበት ሁኔታ እንዲመለሱ ሊደረግ እንደሚገባ ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1815 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻል በመሆኑ የስር ፍ/ቤት በዚህ ረገድ ክርክርና ማስረጃ ሳይመረምር መወሰኑ ህጉንና ክርክሩን የሚመራበት ሥርዓት የተከተለ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

ተጠሪም ታህሳስ 26 ቀን 2016 ዓ.ም የተጻፈው መልስ ይዘትም የስር ፍርድ ቤት የግዥ ውል አለ ወይስ የለም የሚለውን ተገቢውን ጭብጥ በመያዝ ውሳኔ የሰጠ መሆኑን፤ አመልካች በመመሪያው መሰረት ነው ግዥ የተፈጸመው ቢሉም በመመሪያው መሰረት በመስሪያ ቤቱ የበላይ ሃላፊ ውሳኔ መሰረት ግዥው እንደተፈጸመ የሚያስረዳ ማስረጃ አለማቅረባቸውን፤ አመልካች በተወዳደሩበት በውስን ጨረታ እና ቀሪ በተደረገው የፕሮፎርማ ግዥ አሸናፊ ተብለው ውል ያልተዋዋሉ በመሆኑ ክፍያ ያልተፈጸመላቸው

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

መሆኑን፤ ንብረቱን በሞዴል 19 ገቢ ማድረጋቸው ግራቀኙ ግዥ ፈጽመዋል የሚያስብል አይደለም ሲል የስር ፍርድ ቤት የደረሰበት ድምዳሜ ተገቢ ነው የሚል ነው፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን የሚያጠናክር ጥር 15 ቀን 2016 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገቡ ጋር እንዲያያዝ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ፣ ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እና ቅሬታው ለሰበር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ነጥብ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

በመሰረቱ የአስተዳደር መሥሪያ ቤቶች የሚፈጸሙ ግዥዎችን አስመለክቶ የፌዴራል መንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና አዋጁን ተከትሎ ሰኔ 01 ቀን 2002 ዓ/ም ጀምሮ በፀናዉ የፌዴራል መንግስት ግዥ አፈጻጸም መመሪያ እና ማኑዋል ሥርዓት ነው፡፡ በሌላ በኩል የመንግስት ግዢ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በአንቀጽ 16(5) በተሰጠው ስልጣን መሰረት የኮረና ቫይረስ ወረርሽን በሀገራች ከተከሰተ በሃላ ይህንን ለመከላከል የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ግዢን በተመለከተ የአዋጁን አንቀጽ 51(1)(ረ) የሚያሟላ መሆኑን እንዲሁም ግዢዎቹ በአቅርቦት ዕጥረትና በሌሎች ምክንያቶች ከመደበኛው የግዢ አሠራር ሂደት ውጭ ወይም አንድ ዓይነት ግብዓት ወይም መሳሪያ ወይም አገልግሎት ከአንድ በላይ ከሆኑ አቅራቢዎች ግዢ ለመፈጸም አስገዳጅ ሁኔታ መኖሩን በመ/ቤቱ የበላይ ሃላፊ ሲረጋገጥ ኃላፊው በሚሰጠው ውሳኔ መሰረት ግዢው እንዲፈጸም በልዩ ሁኔታ ፈቅዳል፡፡ ይህ በልዩ ሁኔታ እንዲፈጸም የተፈቀደው ግዢ ሊከተል የሚገባውን መሰረታዊ መርሆዎች በአዋጁ አንቀጽ 5 ስር የተመለከተ ሲሆን ይህም በግዥ አፈጻጸም ረገድ የመንግስት ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለዉን ጥቅም ማስገኘት፣ በአዋጁ በተፈቀደዉ ልዩ አስተያየት ካልሆነ በስተቀር በዕጩ ተወዳዳሪዎች መካከል አድልዎ አለማድረግ፣ ከግዥ ጋር በተያያዘ የሚሰጠዉ ዉሳኔ ግልጽ እና ፍትሐዊ መሆን እንዲሁም ዉሳኔዎችና የተወሰዱ እርምጃዎች ተጠያቂነት የሚያስከትሉ እንደሆኑ ተገንዝቦ መስራትን የሚጠይቅ ነው፡፡

በዚህም መሰረት በአዋጁ አንቀጽ 46(2) እና በመመሪያዉ አንቀጽ 16.24.2 እና 16.27.2 እንዲሁም በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 3168 ስር በጨረታዉ አሸናፊ የሆነ ተጫራች የጨረታዉ አሸናፊ እንደሆነ ተገልጾ የሚላከዉ ድብዳቤ በመንግስት መስሪያ ቤቱ እና በተጫራቹ መካከል እንደዉል ሆኖ ሊያገለግል የማይችል መሆኑን እንዲሁም በመንግስት መሥሪያ ቤቱ እና በተጫራቹ/በአቅራቢዉ መካከል ዉል እንደተፈጸመ የሚቆጠረዉ ዝርዝር ጉዳዮችን ያካተተ ዉል በመስሪያ ቤቱ ኃላፊና በተጫራቹ ሲፈረም ብቻ በመሆኑ የጨረታዉ አሸናፊ በመገለጹ ብቻ ዉል እንደተፈጸመ እንደማይቆጠረው ሁሉ አመልካች ከተጠሪ መ/ቤት የፊት ማስክ፣ ሳኒታይዘር፤ፈሳሽ ሳሙና እና ደረቅ ሳሙና እንዲያቀርቡ ትእዛዝ ደርሶኛል በማለት በ23/10/2012 ዓ.ም ተረክቦኛል በማለት የሚያቀርቡትም በልዩ ሁኔታ እንዲፈጸም ከተፈቀደው እና የግዢ አዋጁ አንጻር ሲታይ በፍ/ሕ/ቁ 1681 - 1695 እንደተመለከተው ተጠሪ አመልካች ለግዢ የሚፈልጋቸውን

ዕቃዎች እንዲያቀርብ ሲያሳውቅ ዉል እንዲዋዋል ጥሪ ማድረግና አመልካችም የቀረበለትን ሀሳብ ተቀብሎ ዉል ለመዋዋል ሲቀርብ የዉል ሀሳብ መኖሩን ከሚያመለከት በቀር ከላይ እንደተመለከተው በመካከላቸው በአስተዳደር አካል የተፈጸመ የግዢ ስምምነት ውል እንዳለ አያስቆጥርም፡፡

በእርግጥ ተጠሪ የቀረበዉን ሀሳብ በመቀበል ዕቃዎቹን መረከቡ በመካከላቸዉ ዉል ተቋቁሟል ለማለት የሚያስችል ሁኔታ እንዳለ ሊቆጠር የሚችል ቢሆንም ከሕዝብ አገልግሎት ሥራ ጋር የተያያዘ እና የአስተዳደር መሥሪያ ቤቱን ሥራ ተካፋይነት ቀጣይነት ባለዉ መልኩ የሚጠይቁ የመንግስት ግዥ ዉሎች እንደአስተዳደር ዉል የሚቆጠሩ በመሆናቸው በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 3167 እና 3168 በልዩ ሁኔታ በተደነገገው እና በአዋጁ 649/201 በተመለከተው መሰረት የአስተዳደር የግዥ ዉል ተቋቋመ ሊባል የሚችለዉ ከተዋዋዮች የሚጠበቀዉ ተሟልቶ የዉሉ ጉዳይ በሚገባ አኳኋን ተጽፎ በመንግስት መስሪያ ቤቱና በአቅራቢው ሲፈረም ብቻ ነዉ ፡፡

ስለሆነም ተጠሪ ለአመልካች ንብረቱን እንዲያቀርቡ መታዘዝ እና በሞዴል ለተጠሪ ገቢ ማድረግ በአመልካች እና ተጠሪ መካከል የአስተዳደር የግዥ ዉል ተቋቋመ ሊባል የሚችል ባለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት አመልካችን ክስ ውድቅ በማድረግ የሰጡት ውሳኔ ከዉጤት አንጻር የሚያስለዉጥ ሆኖ አላገኘነዉም፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ውሳኔ</u>**

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 229016 በቀን 10/06/2015 ዓ.ም የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 273698 12/08/2014 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በማጽናት የሰጠው ትእዛዝ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1//ሀ/መሰረት ጸንቷል ፡፡
2. አመልካች ለተጠሪ በሞዴል 19 አስረክቤአለው የሚሉትን ንብረት እንዲመለስላቸው የመጠየቅ መብታቸውን ይህ ውሳኔ አያስቀርም፡፡
3. አመልካችና ተጠሪ በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

**<u>መዝገቡ ተዘግቷል</u>**፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፍ/ደ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ሰ/መ/ቁጥር---247064

ቀን- ጥቅምት 05 ቀን 2017 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ብርሃኑ መንግስቱ

ማርታ ተካ

**አመልካች**:- ዮሴፍ ጅራታ ቱራ - ጠበቃ ቶለማርያም መገርሣ - ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- የፍትህ ሚኒስቴር ዐ/ሕግ - ጌታቸው አሠፋ - ቀረቡ

መዝገብ ተመርምረዉ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ጉዳዩ ወንጀል ሲሆን የተጀመረዉ ተጠሪ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካችን ጨምሮ በ17 ተከሳሾች ላይ በመሠረተዉ ክስ መነሻነት ሲሆን አመልካች በስር ፍ/ቤት 5ኛ ተከሳሽ ነበር፡፡ የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 255390 ነሐሴ 19 ቀን 2014 ዓ.ም እና ጥቅምት 10 ቀን 2016 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በተሰጠ ዉሳኔ የጸናዉ የጥፋተኝነትና የቅጣት ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በሚል ነዉ፡፡

በስር ፍ/ቤት አመልካችን ጨምሮ ተሻሽሎ በቀረበዉ ክስ ስማቸዉ ከ1ኛ እስከ 14ኛ ተራ ቁጥር ያሉትን ተከሳሾችን የሚመለከተዉ 1ኛ ክስ ሆኖ ይዘቱም፡- የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1/ሀ)፣ 35፣ 38

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

እና የፀረ-ሽብር አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 3(3) የተመለከተዉን በመተላለፍ የኦነግ ሸኔን የፖለቲካ ወይም የርዕዮተ ዓለም አላማ ለማራመድ በማሰብ ሕዝብን ወይም የተወሰነ የህብረተሰብን ክፍል ለማሸበር ወይም መንግስትን ለማስገደድ በማሰብ የወንጀሉ ድርጊት በሚሰጠዉ ዉጤት ሙሉ ተካፋይ በመሆን እና ዉጤቱን የራሳቸዉ በማድረግ፤ ወንጀሉን በቀጥታ በመፈጸምና ቀድመዉ ስምምነት በማድረግ በደምቢዶሎ ዩንቨርስቲ ዉስጥ የተፈጠረዉን የተማሪዎችን ግጭት በመፍራት ወደ ቤተሰቦቻቸዉ የሚመለሱ የአማራ ክልል ተማሪዎችን ማገት አለብን በሚል ከሕዳር 22 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ በተለያዩ የቄለም ወለጋ ዞን ሰዩ ወረዳ ማጣ ቀበሌ ላይ ገመዳ ረጋሳ፣ 13ኛ ተከሳሽ ጌታቸዉ የናስ፣ ግርማ ይገዙ፣ አህመዲን ኢተፋ፣ ሞሴ ደጉማ፣ ኢብሳ በቀለ፣ ጃል ኡርጅ፣ ጃል ጉቱ፣ ኬኔሳ ዮናስ፣ 14ኛ ተከሳሽ ኦብሳ ፉፋ እና ሌሎች የኦነግ ሸኔ አባላትና አመራሮች ተሰብስበዉ ከተወያዩ እና ከተስማሙ በኃላ፡-

1ኛ፡- ህዳር 24 ቀን 2012 ዓ.ም በግምት ከቀኑ 7፡00 እስከ 8፡00 ሰዓት በሚሆንበት ጊዜ በኦሮሚያ ክልል ቄለም ወለጋ ዞን ሰዩ ወረዳ ሜንኮ ቀበሌ ቧንቧ ከተባለው ቦታ አካባቢ የአማራ ተወላጅ የሆኑ የደምቢዶሎ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የተፈጠረውን ግጭት በመፍራት ከደምቦዶሎ ከተማ ወረዳ መቻራ ከተማ 16ኛ ተከሳሽ ርስቁ አብደላ በሚያሽከረክረው ኮድ 3-34629 ኦሮ በሆነ ቀይ ዶልፊን ተሳፍረው ወደ ቤታቸው በመሄድ ላይ የነበሩትን ሞናሞን በላይ፣ ጤናለም ሙላቱ፣ ሳምራዊት ቀሬ፣ አሳቤ አያል እና የአካባቢው ነዋሪ የሆነችው ትእግስት መሳይ እንዲሁም ለጊዜው በውል ያልተለዩ ሴቶችን አመልካችን ጨምሮ ከ1ኛ እስከ 8ኛ ተራ ቁጥር የተገለጹ ተከሳሾች ካልተያዙ ግብራብሮቻቸው ጋር በመሆን ዱላ እና የጦር መሳሪያ ታጥቀው የሚሄዱበትን መኪና መንገድ ላይ አስገድደው በማስቆም 4ኛው ተከሳሽ የመኪናውን ቁልፍ ሲነቅል ሌሎች ተከሳሾች ደግሞ መኪናውን በመፈተሸ የኦሮሚኛ ቋንቋ የማይችሉ ወይም አማርኛ ቋንቋ ብቻ የሚችሉትን በመለየትና ከመኪና በማስወረድ ጠልፈው ወይም አግተው በአካባቢው ወደ ሚገኘው ጫካ ይዘው የሄዱና ለኦነግ ሸኔ የበላይ አመራሮች ያስረከቡ በመሆኑ፤

2ኛ፡- ሕዳር 25 ቀን 2012 ዓ.ም በግምት ከቀኑ 7፡00 ሰዓት ሲሆን በቄለም ወለጋ ዞን አንፍሎ ወረዳ ሱዲ ቀበሌ ተብሎ በሚጠራዉ አካባቢ የአማራ ተወላጅ የሆኑ የደምቢ ዶሎ ዩንቨርስቲ ተማሪዎች በዩንቨርሲቲዉ ዉስጥ የተፈጠረዉን ግጭት በመፍራት ከደንቢ ዶሎ ከተማ ወደ ጋምቤላ ከተማ አቅጣጫ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 3-35136 ኦ.ሮ በሆነ ቀይ ዶልፊን ተሳፍረዉ ወደ ቤተሰቦቻቸዉ በመሄድ ላይ የነበሩትን በላይነሽ መኳንንት፣ ስርጉት ጌጤ፣ ዉዴ ግርማዉ፣ ገርማሽ የኔነህ፣ አስካሉ (የማታ) ቸኮል፣ ግርማ ሀብቴ እና ለግዜዉ በዉል ያልተለዩ ተማሪዎችን ከላይ በተጠቀሰዉ ቦታ ላይ ከ9ኛ እስከ 12ኛ የተጠቀሱ ተከሳሾች እና ሌሎችም ለጊዜዉ ካልታወቁ በርካታ የኦነግ ሸኔ አባላት ግብረ-አበሮች ጋር የጦር መሳሪያና ዱላ ይዘዉ የሚሄዱበትን መኪና መንገዱ ላይ በማስቆምና መኪናዉን በመፈተሽ ኦሮምኛ ቋቋ የማይችሉ ወይም አማርኛ ቋንቋ ብቻ የሚናገሩትን መታወቂያ ወረቀታቸዉን በማየትና በመለየት አምስት ሴቶችና ወንድ የደምበ ዶሎ ዩንቨርስቲ ተማሪዎችን ከተሽከርካሪዉ በማዉረድና በመደብደብ ጠልፈዉ ወይም አግተዉ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ለ12ኛ እና 14ኛ ተከሳሾች እንዲሁም ለሌሎች የኦነግ ሸኔ አባላት አስረክበዉ እነርሱ ደግሞ በበኩላቸዉ የታገቱትን ተማሪዎች ለጊዜዉ ላልታወቁ ለኦነግ ሸኔ አመራሮች ያስረከቧቸዉ በመሆኑ፤ በአጠቃላይ ህዳር 24 እና 25 ቀን 2012 ዓ.ም ከላይ ስማቸዉ የተገለጹትን 16 የአማራ ክልል ተማሪዎችን በማገት ለኦነግ ሸኔ አሸባሪ ቡድን የበላይ አመራሮች በትግል ስማቸዉ፡- 1ኛ ጃል መሮ፤ 2ኛ ጃል ሮባ፤ 3ኛ ጃል ጉራራ፤ 4ኛ ጃል ኡርጂ፤ 5ኛ ጃል ፊንድሼ ለተባሉትና ለጊዜዉ ላልታወቁ የሸኔ አሸባሪዎች አሳልፈዉ የሰጡ በመሆኑ ተከሳሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን በፈፀሙት የሽብር ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው፡፡

ተከሳሾች የእምነት ክህደት ቃላቸዉን ሲጠየቁ በክሱ የተገለጸዉን የወንጀል ድርጊት አለመፈጸማቸዉን ገልጸዉ ጥፋተኛ አለመሆናቸዉን በማስመዝገባቸዉ በስር ፍ/ቤት ዐ/ህግም በአመልካች ላይ አንድ ምስክር አቅርቦ ያሰማ ሲሆን ችሎቱም ምክንያቶቹን በመግለፅ የዐ/ህግ ምስክር እንደ ክሱ አስረድቷል በሚል አመልካች ሊከላከሉ ይገባል በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ አመልካችም የመከላከያ ምስክሮችን በማቅረብ ወንጀሉን አለመፈጸዉን አስመልክቶ አሰምተዋል፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃዎች መርምሮ አመልካች ባሰማቸዉ የመከላከያ ማስረጃዎች ፈፅመዉታል ስለተባለው ወንጀል አለመፈፀሙን በማስረዳት የተከላከሉት ነገር የለም በማለት በወ/ሕጉ 32/1/ሀ፣ 35፣ 38 እና የፀረ-ሽብር አዋጁ ቁጥር 1176/2012 አንቀጽ 3(1/ሐ) የተመለከተዉን ተላልፈዋል በሚል አመልካችን ጨምሮ 4 ተከሳሾችን ጥፋተኛ በማድረግ እያንዳንዳቸዉ በ11 ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጡ በአብላጫ ድምፅ ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ የጥፋተኝነትና ቅጣት ዉሳኔ ቅር ተሰኝተዉ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በተናጠል ይግባኝ ቢያቀርቡም የስር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ በዚህ የጥፋተኝነትና ቅጣት ዉሳኔ ባለመስማማት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

አመልካች ግንቦት 09 ቀን 2015 ዓ.ም የተዘጋጀ 4 ገጽ የሰበር አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን ይዘቱ በአጭሩ፡- የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ምንም እንኳን አመልካች በአንድ የሰው ምስክር ብቻ የተመሰረተበት ቢሆንም ከወንጀሉ ክብደት፤ በህብረተሰቡ ብሎም በአገር ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅኖ ጭምር ከግምት በማስገባት የቀረበበት ክስ እና ማስረጃ እንዲከላከል በሚል የሰጠው ብይን የማስረጃ ምዘና መሰረታዊ መርሆችን መሰረት ያላደረገ ስለሆነ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡ አመልካች የተከሰሰበትን ወንጀል መፈጸሙን ዐ/ሕግ በበቂ ማስረጃ ያስረዳዉ ነገር የለም፡፡ ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች ክሱን እንዲከላከል ብይን ሲሰጥ ዐ/ሕግ ያቀረበዉ ማስረጃ በቂ መሆኑን ተጠራጥሯል፡፡ ይህም በፍርድ ክፍሉ "ምንም እንኳን አመልካቾች በአንድ አንድ የሰዉ ምስክሮች ብቻ የተመሰከረባቸዉ ቢሆንም" ሲል የተጠቀመዉ አገላለጽ በአመልካች ላይ የዐ/ሕግ ምስክሩ የሰጠዉን የምስክርነት ቃል ፍ/ቤቱ የተጠራጠረዉ መሆኑንና በቂ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አለመሆኑን የሚያሳይ ነዉ፡፡ ስለሆነም አመልካች በቂ ባልሆነ ማስረጃ እንዲከላከል ተብሎ የተሰጠዉ ብይን በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 141 እና ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 89676 በሰጠዉ አስገዳጅ ትርጉም መሠረት ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡

በስር ፍርድ ቤት ለብይኑ መሰረት ያደረገው የዐ/ሕግ የምስክር ቃል ተዓማኒነት የሌለው እና ምስክሩ ከአመልካች ጋር ፀብ እንዳላቸው ገልፀው የሰጡት የምስክርነት ቃል በቂም በቀል የተሰጠ በመሆኑ፤ እንደዛም ባይባል እንኳን የዐ/ሕግ ምስክር የአመልካች ድምፅ ሰማሁ ያለው በቀን 27/03/2012 ዓ.ም ሆኖ አመልካች ፈፅሞታል የተባለው ወንጀል በክሱ ላይ የተገለፀው በቀን 24/03/2012 ዓ.ም በመሆኑ እንደ ክሱ አልተመሰከረም፡፡ ምስክሩ በወቅቱ እራሱ በኦነግ ሸኔ ታግቼ ታስሬ ጫካ ዉስጥ ነበርኩኝ የአመልካችን ድምጽ በ10 ሜትር ርቀት ላይ ሆኜ ሰምቻለሁ፤ በአይን አላየኃቸዉም ያለ ሲሆን እራሱ ታግቶ ታስሮ ያለ ሰዉ እራሱ በከፍተኛ ጫና ዉስጥ እያለ በአስር ሜትር ርቀት ላይ በጫካ ዉስጥ የሰዉን ድምጽ ሰምቶ ይለያል ተብሎ በማንኛዉም ምክንያታዊ ሰዉ አይገመትም፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቱ ይህንን የምስክርነት ቃል መሰረት በማድረግ ክሱን እንድከላከል የሰጠው ብይን ተገቢ አይደለም፡፡

አመልካች ያቀረባቸዉ ሁለት የመከላከያ ምስክሮች ከዐ/ሕግ ምስክሩ ፀብ ያላቸዉና ምስክርነቱን በቂም በቀል የመሠከረ መሆኑን፤ ምስክሩ ሕዳር 27 ቀን 2012 ዓ.ም የአመልካችን ድምጽ በጫካ ዉስጥ ሆኜ ሰምቻለሁ ባለበት ቀን ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እስከ 11፡00 ሰዓት ከሌሎች ሰዎች ጋር ሽምግልና ላይ የነበረ መሆኑን በሚገባ አስረድቷል፡፡ የዐ/ሕግ ብቸኛ ምስክር የሆነዉ ኑራ መሐመድ ከአመልካች ጋር ጸብ ያለዉ መሆኑን በራሱ በምስክርነቱ ወቅት ያረጋገጠ ሲሆን አመልካችም ይህንኑ አስረድቷል፡፡ ይሁን እንጂ የስር ፍ/ቤቱ "ምስክሩ በአመልካች እና ሌሎች የስር ተከሳሾች ላይ ቂም ይዞ የሚመሰክርበት በቂ ምክንያት አለ ለማለት አልተቻለም" በማለት የመከላከያ ምስክሮች ምስክርነት ቃል በአብላጫ ድምጽ ዉድቅ ተደርጎ የተሰጠዉ የጥፋተኝነት ዉሳኔ ተገቢ አይደለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት መከላከያ ማስረጃዉን ውድቅ በማድረግ የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ የማስረጃ ምዘና ስርዓት መርሆን ያልተከተለ ስለሆነ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በነፃ እንድሰናበት እንዲወሰንልኝ፡፡ ይህ የሚታለፍ ከሆነ የቅጣት ውሳኔ በተመለከተ የወንጀሉ አፈፃፀም ከባድና ውስብስብ የሚባል አለመሆኑ፤ የወንጀሉን ማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮች መልሶ እንደቅጣት ማክበጃ መያዙ እና ደረጃውም ከፍተኛ በማለት መያዙ እንዲሁም ሁለት የቅጣት ማክበጃ መያዙ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ የወንጀሉ ደረጃ ቀላል ተብሎ ተይዞልኝ ቅጣቱ ቀልሎ እንዲወሰንልኝ በማለት የሰበር አቤቱታዉን አቅርቧል፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ የስር ፍ/ቤት አመልካች ክስ የቀረበበትን የወንጀል ድርጊት መፈጸሙን አስረድቷል የተባለዉ 9ኛ የዐ/ሕግ ምስክር ሆኖ አመልካች ድርጊቱን መፈጸሙን ያወቀዉ ጫካ ዉስጥ በ10 ሜትር ርቀት ላይ የአመልካችን ድምጽ ሰምቶ መሆኑን እና ከአመልካች ጋር ጸብ ያላቸዉ መሆኑን ደልጾ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የሰጠዉ ምስክርነት ቃል ሆኖ እያለ ማስረጃዉ በቂ ነዉ ተብሎ አመልካች ተከላከል ተብሎ በስር ፍ/ቤት ብይን መስጠቱ ከወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 141 ድንጋጌ መስፈረት አንጻር ተገቢ ነዉ ወይስ አይደለም? እንዲሁም የወንጀሉ ደረጃ ከባድ የመባሉና የተያዙ የቅጣት ማክበጃዎች ተገቢነት ለማጣራ ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ነዉ፡፡

ተጠሪ ሕዳር 27 ቀን 2016 ዓ.ም የተዘጋጀ 4 ገጽ መልስ ያቀረበ ሲሆን ይዘቱ በአጭሩ፡- ወንጀሉ በአመልካች መፈፀሙን የዐ/ሕግ ማስረጃ በአግባቡ አስረድቷል፡፡ ፍርድ ቤቱ ማስረጃውን ሲመዘን የወንጀል ክብደት እና አሉታዊ ተፅእኖን ከግምት ያስገባ መሆኑን መግለፁ አግባብነት ያለው ነው የሚል እምነት ባይኖረንም የተሰማው ምስክር ግን እምነት የሚጣልበት ነው፡፡ የተሰማው ምስክር አንድ ብቻ መሆኑ ማስረጃው ተቀባይነት እንዳይኖረው የሚያደርግበት የማስረጃ ምዘና አካሄድ የለም፡፡ ምስክሩ በወቅቱ ታግቶ የነበረ እና ከታገተበት ቦታ ላይ የታገቱ ሰዎችን አመልካች እና ሌሎች ሰዎች ይዘው የመጡ መሆኑን የመሰከረው በወቅቱ በቦታው የነበረ በመሆኑ ነው፡፡

አመልካች እና የዐ/ሕግ ምስክር አስቀድሞ ፀብ ነበራቸው መባሉ ብቻ በቂም በቀል የተሰጠ የምስክርነት ቃል ነው ተብሎ ሊወሰድ አይገባም፡፡ በሌላ በኩልም የአመልካች ምስክሮች የሰጡት ቃል እርስ በርስ የሚጣረስ በመሆኑ አመልካች የተከሰሰበት ወንጀል ለማስተባበል በቂ አይደለም፡፡ ቃላቸዉን ሲሰጡ አመልካች እና የዐ/ሕግ ምስክር በሽምግልና ምስክሩ ገንዘብ እንዲመልስ ስለተደረገ በዚህ ቂም ይዞ ነዉ ያሉ ሲሆን ገንዘብ እንዲመልስ የተደረገዉ በሽምግልና ከሆነ በመካከላቸዉ ዕርቅ የተፈጸመ መሆኑንና ገንዘብም የመለሰዉ በዕርቅ ስምምነቱ መሠረት እንጂ ተገዶ አለመሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ሽምግልና የተቀመጠዉም አመልካች ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ሰዎች ሆነዉ ሳለ አመልካች ላይ ብቻ ቂም የሚያዝበት ሁኔታ አይኖርም፡፡ ስለዚህ መከላከያ ምስክሮቹ አቋም በመያዝ በቂም በቀል የተሰጠ ምስክርነት ነዉ በሚል መመስከራቸዉ ገለልተኛ ሆነዉ አለመመስከራቸዉን የሚያሳይ ነዉ፡፡ በመሆኑም የአመልካች የመከላከያ ምስክሮች የሰጡት ቃል ወገንተኝነት የታየበት በመሆኑ በስር ፍ/ቤት አመልካች ጥፋተኛ ተብሎ የተሰጠው ፍርድ የሚነቀፍ አይደለም፡፡

የስር ፍ/ቤት ከቅጣት አወሳሰን በተመለከተ ድርጊቱ የተፈፀመው በተማሪዎች ላይ መሆኑ፤ ተላልፈው የተሰጡትም ለሸኔ የሽብር ቡድን መሆኑ እና ተማሪዎች ያሉበት ሁኔታ አለመታወቁ እንዲሁም የቤተሰብ ጭንቀት ሲታይ ከባድ ያደርገዋል፡፡ የወንጀል ድርጊቱ የተፈፀመው ማንነትን መሰረት ባደረገ መልኩ ነው፤ ይህ ደግሞ የሽብር ወንጀል ማቋቋሚያ አይደለም፤ በቅጣት አወሳሰን ረገድ በስር ፍ/ቤት የተሰራ ስህተት የለም በማለት የቀረበው አቤቱታ ውድቅ እንዲሆን እና የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት የጥፋተኝነት ፍርድ እና የቅጣት ውሳኔ እንዲፀና በመጠየቅ ተከራክሯል፡፡ አመልካች ታሕሳስ 05 ቀን 2016 ዓ.ም የተዘጋጀ 2 ገጽ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታዉን በሚያጠናክር መልኩ አቅርቧል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን የአመልካችን አቤቱታ ከስር ፍ/ቤቶች ዉሳኔና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ አቤቱታቸዉ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡ ምላሽ የሚያሻቸዉ ጭብጦች፡-

1. የስር ፍ/ቤት አመልካች ክስ የቀረበበትን የወንጀል ድርጊት መፈጸሙን አስረድቷል የተባለዉ 9ኛ የዐ/ሕግ ምስክር ሆኖ አመልካች ድርጊቱን መፈጸሙን ያወቀዉ ጫካ ዉስጥ በ10 ሜትር ርቀት ላይ የአመልካችን ድምጽ ሰምቶ መሆኑን እና ከአመልካች ጋር ጸብ ያላቸዉ መሆኑን ደልጾ የሰጠዉ ምስክርነት ቃል ሆኖ እያለ ማስረጃዉ በቂ ነዉ ተብሎ አመልካች ተከላከል ተብሎ በስር ፍ/ቤት ብይን መሰጠቱ ከወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 141 ድንጋጌ መስፈረት አንጻር ተገቢ ነዉ ወይስ አይደለም? እንዲሁም
2. የቅጣት ውሳኔ የተላለፈበት አግባብ በተመለከተ በተለይም የወንጀሉ ደረጃ ከባድ የመባሉና የተያዙ የቅጣት ማክበጃዎች ተገቢ ናቸዉ ወይስ አይደሉም? የሚሉት ናቸዉ፡፡

የመጀመሪያዉን ነጥብ በተመለከተ፡- አመልካች በክሱ ላይ የተጠቀሰው የወንጀል ድርጊት መፈፀሙን ዐቃቤ ህግ ተቀባይነት ባለው የማስረዳት ደረጃ ልክ ማስረዳቱ ተረጋግጧል ወይስ አልተረጋገጠም? የሚለዉ ሲሆን በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 20(3) ድንጋጌ መሠረት አንድ ተከሳሽ ነጻ ነው ተብሎ የመገመት መብት ያለዉ በመሆኑ ዐ/ሕግ በክሱ የተገለጸዉን የወንጀል ድርጊት ተከሳሽ የፈጸመ መሆኑን በቅድሚያ የማስረዳት ህጋዊ ግደታ ያለበት መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ አንድ ሰው ለወንጀል ድርጊት ኃላፊ ተብሎ ቅጣት ሊወሰንበት የሚገባው ወንጀሉ መስራቱ ወይም መፈፀሙና ተሰራ ወይም ተፈፀመ የተባለው ወንጀል ደግሞ በተከሳሹ መፈፀሙ በበቂና በአሳማኝ ሁኔታ ሲጋገጥ ስለመሆኑ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23(4)፤ 32፣ 40፤ 57፣ 58(1) እና ከወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 141፣142 እና 149 ድንጋጌዎች አገላለፅና መንፈስ መገንዘብ የሚቻል ጉዳይ ነው፡፡ ማንም ሰው በዋና ወንጀል አድራጊነት ወንጀል እንዳደረገ የሚቆጠረው ወንጀሉን እርሱ ራሱ በቀጥታ ቢያደርግ ወይም በቀጥታ ባያደርግም እንኳን በመላ ሀሳቡና አድራጎቱ በወንጀሉ ድርጊትና በሚሰጠው ውጤት ሙሉ ተከፋይ በመሆን ወንጀሉን የራሱ ያደረገ ሆኖ ሲገኝ እንደሆነ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ለ/ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ከሳሽ የሆነው ዐ/ሕጉም ይህንኑ በሕጉ የተጣለበትን ግዴታ መወጣት እንዳለበት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 97203 አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለዉ ዐ/ሕግ ክሱንና የተከሳሽን የወንጀል ተሳትፎ በቂና አሳማኝ ሁኔታ የማስረዳት ግዴታዉን ባልተወጣበት አንድን ተከሳሽ እንዲከላከል ብይን መስጠቱም ሆነ ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ ጥፋተኛ ሊደረግና ሊቀጣ እንደማይገባዉ ነዉ፡፡

በሌላ በኩል አንድ ተከሳሽ የወንጀል ድርጊቱን በቀጥታ ሲፈጽም ያየ የዓይን ምስክር ባይኖርም ድርጊቱ ሲፈጸም ድምጽ በጆሮ በመስማት ወይም የአከባቢ ሁኔታ ማስረጃ ወንጀሉን የፈጸመው ተከሳሽ መሆኑንና ከተከሳሽ ውጭ ሌላ ሰው ወንጀሉን ሊፈጽመው አይችልም የሚል መደምደሚያ ላይ ለማድረስ በቂና አሳማኝ በሆነ ሁኔታ የሚያስርዳ ሆኖ ሲገኝ የአስረጅነት ብቃት ያለው ማስረጃ ተደርጎ እንደሚወሰድ የማስረጃ ብቃት መስፈርትና የማስረጃ አመዛዘን መርሆች ያሳያሉ፡፡ አንድ ምስክር በጆሮ የሰማዉ ድምጽ የተከሳሹን ማንነት ለመለየት ብቃት ያለዉ ማስረጃ ነዉ ወይስ አይደለም የሚለዉን ለመመዘን ድምጹ የተሰማበት ሁኔታ፣ የተጠርጣሪዎች ብዛት፣ ምስክሩ ከድምጹ ጋር አስቀድሞ የነበረዉ ትዉዉቅ፣ ምስክሩ ተራ ሰዉ ነዉ ወይስ ድምጽ የሚለይ ባለሙያ ወይም የፖሊስ አባል፣ እንዲሁም ሌሎችን አካባቢያዊ ሁኔታዎች ግምት ዉስጥ ያስገባ መሆን ይጠበቅበታል፡፡ ከአንድ ምስክር ይልቅ ሁለት እና ከዚያ በላይ ምስክሮች አንድን ፍሬ ነገር በማረገገጥ የሰጡት ምስክርነት የበለጠ ክብደት ሊሰጠዉ የሚችልበት ሁኔታ ቢኖርም አንድ ምስክር የሰጠዉ ቃል ታአማኒነቱ ጠንካራ እስከሆነ ድረስ በቂና አሳማኝ አይደለም ለማለት ብቻዉን በቂ አይደለም፡፡

ከላይ ከተገለጸዉ አንጻር መገንዘብ የሚቻለዉ አመልካች በክሱ በተገለጹት የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ላይ የተፈጸመዉን ተማሪዎችን አግቶ ወደ ጫካ ይዞ በመሄድና ለኦነግ ሸኔ የበላይ አመራሮች የማስረከብ ድርጊት የነበረዉን ተሳትፎ እና ሚናን ተጠሪ በቂና አሳማኝ ማስረጃ በማቅረብ የማስረዳትና የማረጋገጥ ግደታ ያለበት ሲሆን ተጠሪ ይህንን የማስረዳት ግደታውን በአግባቡ ካልተወጣ፣ አመልካች የተጠሪን ማስረጃ የመከለካልም ሆነ የማስተባበል ግደታ የሌለበት መሆኑን በተለይ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 141 ድንጋጌ ይዘትና መሰረታዊ አላማ መረዳት የሚቻል መሆኑን ነዉ፡፡

አመልካች ክስ የቀረበባቸዉ ሕዳር 24 ቀን 2012 ዓ.ም የጠለፋ ወይም የዕገታ ተግባር ተፈጸመባቸዉ የተባሉትን የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ከ1ኛ እስከ 8ኛ ተራ ቁጥር ከተከሰሱ ተከሳሾችና ካልተያዙ ሌሎች ግብረ-አበሮቻቸዉ ጋር በመሆን ዱላ እና የጦር መሳሪያ ታጥቀዉ ተማሪዎች የሚሄዱበትን መኪና በማስቆም 4ኛ ተከሳሽ አወል ጅብሪል የተባለዉ የመኪናዉን ቁልፍ ሲነቅል አመልካችን ጨምሮ ሌሎች ተከሳሾች ደግሞ መኪናዉን በመፈተሽ የኦሮምኛ ቋንቋ የማይችሉ ወይም አማረኛ ቋንቋ ብቻ የሚችሉትን በመለየትና ከመኪናዉ በማስወረድ ጠልፈዉ ወይም አግተዉ በአካባቢዉ ወደ ሚገኘዉ ጫካ ይዘዉ የሄዱና ለኦነግ ሸኔ የበላይ አመራሮች አስረክበዋል በሚል ሲሆን ዐ/ሕግ የአመልካችን የወንጀል ተሳትፎና ሚና ለማስረዳት ያቀረበዉ አንድ ምስክር ነዉ፡፡ ምስክርነቱም ሕዳር 24 ቀን 2012 ዓ.ም በተፈጸመዉ የእገታ ተግባር ላይ አመልካች በቀጥታ መሳተፉን የሚያረጋግጥ ሳይሆን ከ3 ቀናት በኃላ ሕዳር 27 ቀን 2012 ዓ.ም የታገቱ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን ይዘዉ ሄደዉ ለኦነግ ሸኔ የበላይ አመራሮች ካስረከቡ ሰዎች መካከል አመልካች መኖሩን በድምጹ ለይቻለሁ የሚል ምስክር ነዉ፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ምስክሩም ኑራ መሀመድ የተባለ 9ኛ የዐ/ሕግ ምስክር ሲሆን ምስክርነቱም በኦነግ አባላት ታስሮ ጫካ እያለ በ3ኛ ቀን ሕዳር 27 ቀን 2012 ዓ.ም ብዛታቸዉ በግምት 14 የሚሆኑ ልጃገረዶችን ይዘዉ እንዳመጡና ለጃል ጉራራ ሰጥተዉት እሱም ልጃገረዶችን ሲደበድባቸዉ በአማረኛ እናቴ፣ እናቴ እያሉ ይጮሁ እንደነበር፤ ከተከሳሾች መካከል 5ኛ ተከሳሽ ዮሴፍ ጅራታን(አመልካችን)፣ 6ኛ ተከሳሽ ጋዲሳ ገላቱን እና 7ኛ ተከሳሽ ነብዩ ባበክርን ሲያወሩ ድምጻቸዉን ሰምቶ 10 ሜትር በሚሆን ርቀት ላይ ሆኖ በድምጻቸዉ እንደለያቸዉ፤ ከዚያም ልጆችን ከጃል ጉራራ ወደ ጃል ሮባ ዉሰዷቸዉ ሲባል 5ኛ ተከሳሽ የሆነዉ ዮሴፍ ጅራታ(አመልካች) ልጆችን ከሱዳ አምጥቻለሁ ደክሞኛል እያለ እንደነበር፤ ሆኖም ግን መዉሰድ አለብህ ትዕዛዝ ነዉ ተብሎ ከምሽቱ 1:00 ሰዓት አካባቢ ልጆቹን ወደ ጃል ሮባ የወሰዷቸዉ መሆኑን፤ ከአንድ ወር በኃላ ምስክሩ ከታሰረበት ጫካ አምልጦ እንደወጣና በአሜሪካን ሬዲዮ ልጆቹ የታገቱ መሆኑንና አንዲት ልጅም ያመለጠች መሆኗን መስማቱን፤ ከተከሳሾች መካከል 3ቱን ብቻ በችሎት የለያቸዉ ቢሆንም ከ3ቱም ጋር በንብረት ምክንያት አለመግባባት እንዳላቸዉ፤ ይኸዉም የምስክሩ ንብረት ጠላቴ በሚላቸዉ ሰዎች ሲዘረፍበት 3ቱ ተከሳሾች የነበሩ መሆናቸዉን የመሰከረ ነዉ፡፡

ከዚህ ምስክርነት መገንዘብ የሚቻለዉ አመልካች ሕዳር 24 ቀን 2012 ዓ.ም ተደረገ በተባለዉ የዕገታ ተግባር ወይም የወንጀል ድርጊት በቀጥታ የተሳተፈ ወይም ሚና የነበረዉ መሆኑን የሚያረጋግጥ ምስክርነት ያልተሰጠ ሲሆን ከእገታዉ በኃላ ተማሪዎችን ጃል ጉራራ ለተባለዉ የኦነግ አባል በማስረከብ ረገድ ያለዉን ሚና በተመለከተ ምስክሩ አመልካችንም ሆነ ተማሪዎችን በዓይን አይቶ ለይቷቸዉ ሳይሆን በድምጻቸዉ እና ተማሪዎች ሲደበደቡ በአማረኛ እናቴ፤ እናቴ የሚል ከተናገሩት ንግግርና ከአንድ ወር በኃላ ከአሜሪካን ሬዲዮ ከሰማዉ መረጃ ተነስቶ እነሱ ናቸዉ የሚል ድምዳሜ ላይ መድረሱን ነዉ፡፡ በተለይ በስር ፍ/ቤት አናሳዉ ድምጽ በልዩነት ሀሳቡ ካሰፈረዉ የምስክሩ ቃል በወቅቱ ምስክሩ ታስሮ እየተጠበቀ ስለነበረ ተከሳሾችንም ሆነ ተማሪዎችን በዓይኑ እንዳለየና ይልቁንም 10 ሜትር ርቀት ቦታ ላይ ሆነዉ ተከሳሾቹ ድምጻቸዉን ከፍ አድርገዉ ሲጨቃጨቁ በድምጻቸዉ 3ቱን ተከሳሾች መለየቱን ነዉ፡፡ ይህ ምስክርነት የታገቱትን ተማሪዎቹን ጃል ጉራራ ለተባለዉ የኦነግ አባል ወስደዉ ካስረከቡ የድርጊቱ ፈጻሚዎች ዉስጥ አመልካችን ጨምሮ 3ቱም ተከሳሾች መኖራቸዉን ቀርቶ ድምጻቸዉ ተሰማ የተባሉ ልጃገረዶች በክሱ የተገለጹ ተማሪዎች ስለመሆናቸዉ በበቂና አሳማኝ ሁኔታ ያረጋገጠ አይደለም፡፡

ምስክሩ ከ3ቱም ተከሳሾች ጋር አስቀድሞ ትዉዉቅ የነበረዉ በመሆኑ ድምጻቸዉን ሰምቶ የመለየት ዕድሉ ሰፊ ነዉ ቢባል እንኳ የተከሳሾቹ ስም ሲጠራ ባልሰማበት ወይም ድርጊቱ ተፈጽሟል የተባለዉ መኖሪያ ሰፈራቸዉ ሳይሆን ጫካ ዉስጥ በመሆኑ ከተወሰኑ ተጠርጣሪዎች መካከል የሚለይ ድምጽ ባለመሆኑ ተቀራራቢ ድምጽ ያላቸዉ ብዙ ሰዎች በአካባቢዉ ሊኖሩ የሚችሉበት ዕድል ሰፊ በመሆኑ፤ በተለይ ምስክሩ በእስርና ጥበቃ ስር የነበረ ከመሆኑ እና ሲጨቃጨቁ ሰማሁ ከሚል በቀር የአመልካችን ድምጸት የሚመስል እኔ ከዚያ አምጥቻቸዋለሁ፤ ደክሞኛል ከዚህ በኃላ መዉሰድ አልችልም ያለዉ አመልካች ነዉ፤ በቦታዉ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ተገኝተዋል የሚል ድምዳሜ ላይ ቢደረስ እንኳ በሽብር ወንጀሉ አመልካች በፍላጎቱ ፈቅዶ የተሳተፈ መሆኑን በግልጽ የሚያሳይ ባልሆነበት ሁኔታ ምስክርነቱ በቂና አሳማኝ በሆነ መልኩ የአመልካችን ተሳትፎ አረጋግጧል ሊባል የሚችል አይደለም፡፡

በተለይ ደግሞ ምስክሩ በትክክልም በቦታዉ የነበረና የአመልካችን ድምጸት የሚመስል እና የታገቱ ተማሪዎችን ድምጽ ሰምቷል ቢባል እንኳ ንብረቱ ጠላቴ ናቸዉ በሚላቸዉ ሰዎች ሲዘረፍ አመልካችን ጨምሮ 3ቱም ተከሳሾች በቦታዉ የነበሩ በመሆናቸው በመካከላቸዉ ቂም የነበረ መሆኑን ምስክሩ ራሱ ከማረጋገጡ እና የሌላ ወንጀል ፈጻሚን ድምጽ መስማቱን ወይም መለየቱን ገልጾ ባልመሠከረበት ሁኔታ የሰጠዉ ምስክርነት ገለልተኛ ነዉ ሊባል ስለማይችል እንዲሁም ምንም ዓይነት ሌላ ደጋፊ ማስረጃ በሌለበት በስር ፍ/ቤት እንደበቂና እምነት የሚጣልበት ማስረጃ ተደርጎ መወሰዱ ተገቢ አይደለም፡፡

ከላይ ከተገለጸዉ በተጨማሪ የስር ፍ/ቤት አመልካችን ጨምሮ 3ቱ ተከሳሾች እንዲከላከሉ ያለበትን ምክንያት ሲሰጥ ተከሳሾቹ በአንድ ምስክር ብቻ የተመሠከረባቸዉ ቢሆንም ከወንጀሉ ክብደት፣ በሕብረተሰቡ ብሎም በአገር ላይ ሊያሳድር የሚችለዉን አሉታዊ ተጽዕኖ ከግምት በማስገባት ሊከላከሉት የሚገባ ሆኖ ተገኝቷል በማለት በፍርዱ ማስፈሩ ሲታይ የስር ፍ/ቤት የዐ/ሕግ ማስረጃ የአመልካችን ጨምሮ የ3ቱ ተከሳሾችን ተሳትፎ ያላረጋገጠና ፍ/ቤቱን ያላሳመነዉ መሆኑን፤ በተለይም ዐ/ሕግ የማስረዳት ሸክሙን ያልተወጣ መሆኑን የሚያመላክት ነዉ፡፡ በርግጥ ተማሪዎቹ ላይ ማንነታቸዉን መሠረት በማድረግ የተፈጸመዉ እገታና ወንጀል እጅግ ከባድና ሕብረተሰቡ የደህንነት ስሜት እንዳይሰማዉ ያደረገ ቢሆንም በቂና አሳማኝ በሆነ ማስረጃ የወንጀሉ ተሳታፊ መሆናቸዉ ያልተረጋገጠባቸዉን ተጠሪጣሪዎችን እንዲከላከሉ ብይን መስጠትም ሆነ ጥፋተኛ አድርጎ መቅጣት በወንጀል ድርጊቱ የሌሉትን ንጹሀን ሰዎች እንዲቀጡ በማድርግ ከሚያስከትለዉ ጉዳት ባሻገር እዉነተኛ ወንጀል ፈጻሚዎች ከፍትህ እንዲያመልጡ አስተዋጽኦ የሚያደርግ በመሆኑ ስህተት ነዉ፡፡ በመሆኑም አመልካች ክሱን እንዲከላከል ብይን የተሰጠዉም ሆነ ጥፋተኛ ተብሎ እንዲቀጣ የተሰጠዉ ዉሳኔ ዐ/ሕግ የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 141 በሚያስቀምጠው የማስረጃ መለኪያ መስፈርት መሰረት የአመልካችን የወንጀል ተሳትፎ ባላስረዳበትና በሕጉ የተጣለበትን ግዴታ ባልተወጣበት ሁኔታ በመሆኑ በስር ፍ/ቤት አመልካች እንዲከላከል የተሰጠዉ ብይን፣ የጥፋተኛነትና የቅጣት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ሊታረም እና አመልካች ላይ የተላለፈዉ ዉሳኔ ሊሻር የሚገባዉ ሆኖ ተገንቷል፡፡

ከላይ በ2ኛ ተራ ቁጥር የተያዘዉን ጭብጥ በተመለከተ በአንደኛዉ ጭብጥ አመልካች መከላከል ሳያስፈልጋቸዉ በነጻ ሊሰናበት ይገባ ነበር በመባሉ በቅጣት ዉሳኔ ረገድ በስር ፍ/ቤት መሠረታዊ የሕግ ስህተት መፈጸም አለመፈጸሙን መመርመር አስፈላጊ ባለመሆኑ ታልፏል፡፡

ሲጠቃለል በስር ፍ/ቤት አመልካች ክሱን እንዲከላከል ብይን የተሰጠዉም ሆነ ጥፋተኛ ተብሎ እንዲቀጣ ዉሳኔ የተሰጠዉ ዐ/ሕግ የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 141 በሚያስቀምጠው የማስረጃ መለኪያ መሰረት የአመልካችን ተሳትፎ ባላስረዳትና በሕጉ የተጣለበትን ግዴታ ባልተወጣበት ሁኔታ በመሆኑ በስር ፍ/ቤት አመልካች እንዲከላከል የተሰጠዉ ብይን፣ የጥፋተኛነትና የቅጣት ዉሳኔ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23(4)፤ 32፣ 40፤ 57፣ 58(1) እና ከወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 141፣142 እና 149 ድንጋጌዎችን እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 97203 እና በሌሎች መዛግብት የሰጠዉን ገዥ ትርጉም ያላገናዘበ፤ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ለ እና ሸ) እና አንቀጽ 10(1) መሠረት መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 255390 ነሐሴ 19 ቀን 2014 ዓ.ም እና ጥቅምት 10 ቀን 2015 ዓ.ም ተሰጥቶ፤ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 237078 መጋቢት 14 ቀን 2015 ዓ.ም በተሰጠ ዉሳኔ የጸናዉ አመልካችን አስመልክቶ የተሰጠዉ የጥፋተኝነትና የቅጣት ዉሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1/ለ) እና በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 195(2) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት 5ኛ ተከሳሽ የነበረዉ ዮሴፍ ጅራታ ቱራ በሽብር ወንጀሉ ተሳታፊና ሚና የነበረዉ መሆኑ በበቂና አሳማኝ ሁኔታ ስላልተመሰከረበት በስር ፍ/ቤቶች የተላለፈበት የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ቁጥር 195(2)(ለ-1) መሰረት ሙሉ በሙሉ በመሻር በነጻ እንዲሰናበት ተወስኗል፡፡ አመልካቹ በሌላ ወንጀል የማይፈለግ መሆኑ ከተረጋገጠ ወዲያውኑ ከእስር እንዲፈታ ተገልፆ የመፍቻ ትዕዛዝ ለክፍሉ ማረሚያ ቤት ይድረሰው ብለናል፡፡ ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሠ/መ/ቁጥር 247066

ጥቅምት 05 ቀን 2017ዓ/ም

**ዳኞች ፡- ብርሀኑ አመነው**

**በዕዉቀት በላይ**

**ቀነዓ ቂጣታ**

**ብርሃኑ መንግሥቱ**

**ማርታ ተካ**

**አመልካች፡- ከሊፋ አብዱራህማን**

**ተጠሪ ፡- ፍትሕ ሚኒስቴር - ዐቃቤ ሕግ**

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል።

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በወንጀል ክርክር የሚቀርቡ ማስረጃዎች የሚመዘንበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ክርክሩ የተጀመረው በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ በአመልካች ላይ እና በሌሎች 16 ሰዎች ላይ በመሠረተዉ የወንጀል ክስ ሲሆን አመልካች 1ኛ ተከሳሽ ነበር፡፡የቀረበበትም ክስ ይዘት፡- አመልካች ከሌሎች ተከሳሾች ጋር በመሆን የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1/ሀ)፣ 35፣38 እና የፀረ ሽብር አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀፅ 3/3 ላይ የተደነገገዉን በመተላለፍ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር(ኦነግ) ሸኔን የፖለቲካ ወይም የርዕዮተ አለም ዓላማቸውን ለማራመድ በማሰብ ሕዝብን ወይም የተወሰነ የኅብረተሰብ ክፍል ለማሸበር ወይም መንግስትን ለማስገደድ በማሰብ የወንጀሉ ድርጊት በሚሰጠው ውጤት ሙሉ ተካፋይ በመሆን እና ውጤቱን የራሳቸው በማድረግ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ወንጀሉን በቀጥታ በመፈጸምና ቀድመው ስምምነት በማድረግ በደምቢዶሎ ዩንቨርስቲ ውስጥ የተፈጠረውን የተማሪዎች ግጭት በመፍራት ወደ ቤተሰቦቻቸው የሚመለሱ የአማራ ክልል ተማሪዎችን ማገት አለብን በሚል ከቀን 22/03/2012ዓ.ም ጀምሮ በተለያዩ የቄለም ወለጋ ዞን ሰዮ ወረዳ ማጣ ቀበሌ ላይ ገመዳ ረጋሳ፣13ኛ ተከሳሽ ጌታቸው ዮናስ፣ግርማ ይገዙ፣አህመዲን ኢተፋ፣ሞሴ ደጉማ፣ኢብሳ በቀለ፣ጃል ኡርጅ፣ጃል ጉቱ፣ኬኔሳ ዮናስ፣14ኛ ተከሳሽ ኦብሳ ፉፋ እና ሌሌች የኦነግ አባላትና አመራሮች ተሰብስበው ከተወያዩ እና ከተስማሙ በኋላ፡-1ኛ) በቀን 24/03/2012ዓ.ም በግምት ከቀኑ 7፡00 እስከ 8፡00 ሰዓት በሚሆንበት ጊዜ በኦሮሚያ ክልል ቄለም ወለጋ ዞን ሰዮ ወረዳ ሜንኮ ቀበሌ ቢንቢ ከተባለው ቦታ አካባቢ የአማራ ተወላጅ የሆኑ የደምቢዶሎ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ዩንቨርስቲው ውስጥ የተፈጠረውን ግጭት በመፍራት ከደምቢዶሎ ከተማ ወረዳ መቻራ ከተማ 16ኛ ተከሳሽ ርስቁ አብደላ በሚያሽከረክረው ኮድ 3-34629 ኦሮ በሆነ ቀይ ዶልፊን ተሳፍረው ወደ ቤተሰቦቻቸው በመሄድ ላይ የነበሩትን ሞናሞን በላይ፣ ጤናለም ሙላቴ፣ሳምራዊት ቀሬ፣አሳቤ አያል እና የአካባቢው ነዋሪ የሆነችውን ትእግስት መሳይ እንዲሁም ለጊዜው በውል ያልተለዩ ሴቶችን ከ1ኛ እስከ 8ኛ የተገለፁ ተከሳሾች ካልተያዙ ግብረ አበሮቻቸው ጋር በመሆን ዱላ እና የጦር መሳሪያ ታጥቀው የሚሄዱበትን መኪና መንገድ ላይ አስገድደው በማስቆም 4ኛ ተከሳሽ አወል ጅብሪል የተባለው የመኪናውን ቁልፍ ሲነቅል ሌሎች ተከሳሾች ደግሞ መኪናውን በመፈተሽ የኦሮሚኛ ቋንቋ የማይችሉ ወይም አማርኛ ቋንቋ ብቻ የሚችሉትን በመለየትና ከመኪናው በማስወረድ ጠልፈው ወይም አግተው በአካባቢው ወደሚገኘው ጫካ ይዘው የሄዱና ለኦነግ ሸኔ የበላይ አመራሮች ያስረከቡ በመሆኑ እና 2ኛ) በቀን 25/03/2012ዓ.ም በግምት ከቀኑ 7፡00 ሰዓት ሲሆን በቄለም ወለጋ ዞን አንፍሎ ወረዳ ሱዲ ቀበሌ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የአማራ ተወላጅ የሆኑ የደምቢ ዶሎ ዩንቨርስቲ ተማሪዎች በዩኒቨርስቲው ውስጥ የተፈጠረውን ግጭት በመፍራት ከደምቢዶሎ ከተማ ወደ ጋምቤላ ከተማ አቅጣጫ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 3-35138 ኦሮ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ተሳፍረው ወደ ቤተሰቦቻቸው በመሄድ ላይ እያሉ የነበሩትን በላይነሽ መኳንንት፣ስርጉት ጌጤ፣ውዴ ግርማው፣ግርማሽ የኔነህ፣አስካሉ(የማታ) ቸኮል፣ግርማው ሀብቴ እና ለጊዜው በውል ያልተለዩ ተማሪዎችን ከላይ በተጠቀሰው ቦታ ላይ ሲደርሱ ከ9ኛ እስከ 12ኛ የተጠቀሱ ተከሳሾች እና ሌሎችም ለጊዜው ካልታወቁ በርካታ የኦነግ አባላት ግብረ አበሮቻቸው ጋር የጦር መሳሪያና ዱላ ይዘው የሚሄዱበትን መኪና መንገዱ ላይ በማስቆምና መኪናውን በመፈተሽ ኦሮምኛ ቋንቋ የማይችሉ ወይም አማርኛ ቋንቋ ብቻ የሚናገሩትን የመታወቂያ ወረቀታቸውን በማየትና በመለየት 5 ሴቶችና 1 ወንድ የደምቢዶሎ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን ከተሽከርካሪው በማውረድና በመደብደብ ጠልፈው ወይም አግተው ለ12ኛ እና 14ኛ ተከሳሾች እንዲሁም ለሌሎች የኦነግ ሸኔ አባላት አስረክበው እነርሱ ደግሞ በበኩላቸው የታገቱትን ተማሪዎች ለጊዜው ላልታወቁ ለኦነግ ሸኔ አመራሮች አስረክበዋል፡፡

በአጠቃላይ ህዳር 24 እና 25 ቀን 2012 ዓ.ም በቄለም ወለጋ ዞን ሰዮ ወረዳ እና አንፍሎ ወረዳ ላይ ከላይ ስማቸው የተገለፁትን 16 የአማራ ክልል ተማሪዎችን በማገት ለኦነግ ሸኔ አሸባሪ ቡድን የበላይ አመራሮች

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በትግል ስማቸው -1ኛ ጃል መሮ፣2ኛ ጃል ሮባ፣3ኛ ጃል ጉራራ፣4ኛ ጃል ኡርጂ፣5ኛ ጃል ፈንድሼ ለተባሉትና ለጊዜው ላልታወቁ የሸኔ አሸባሪዎች አሳልፈው የሰጡ በመሆኑ ተከሳሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን በፈጸሙት የሽብር ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው፡፡

አመልካችም የወንጀል ድርጊቱን አልፈፀምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ክዶ በመከራከሩ ዐቃቤ ሕግ በአጠቃላይ 17 ምስክሮችን ቃል አሰምቷል፡፡ በስር ፍርድ ቤት ፍርድ ላይ እንደተመለከተዉ ዐቃቤ ሕግ አቅርቦ ካሰማቸዉ ምስክሮች ዉስጥ 15ቱ ምስክሮች የተጋች ተማሪዎች ቤተሰቦች ሲሆኑ ስለወንጀል ፈጻሚዎች ማንነትም ሆነ ተከሳሾችን እንደማያዉቁ ያረጋገጡ ቢሆንም ግን በወቅቱ የታገቱ የአማራ ክልል ተወላጆች የሆኑ 16 የደንቢዶሎ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች መኖራቸዉን መስክረዋል፡፡የቀረቡት የዐቃቤ ሕግ የሰነድ ማስረጃዎችም ቢሆኑ በዩኒቨርስቲዉ ሲማሩ የነበሩ እና በሕዳር 24 እና 25 ቀን 2012 ዓ/ም ወደ ቤተሰቦቻቸዉ በሁለት አቅጣጫ ሲሄዱ የነበሩት ተማሪዎች መታገታቸዉን የሚያረጋግጡ እንጂ ስለወንጀል ፈጻሚዎች ማንነት ያረጋገጡት አንዳች ነገር ባይኖርም 1ኛ ምስክር አቶ መሳይ መዝገቡ በእለቱ በቀን 24/03/2012ዓ/ም አመልካች ካሊፋ አብዱረህማን እና 8ኛ ተከሳሽ ናስር መሀመድ የሚባሉ ልጆች ከሌሎች ካልታወቁ ሰዎች ጋር በመሆን የተማሪዎች እገታ ወንጀል ላይ መሳተፋቸዉን መስክረዋል፡፡ እኔ ካመለጥኳቸዉ በኋላ በዕለቱ በቀን 24/03/2012 ዓ/ም ዕሮብ ዕለት ከቀኑ 9)) ሰዓት ላይ ካሊፋ የሚባለዉን አንዱን ልጅ ለመከላከያ ያስያዝኩት ሲሆን በማግስቱ በቀን 25/03/2012 ዓ/ም ከቀኑ 10:00 ሰዓት ላይ ደግሞ የጸጥታ ኃይል ሲመጣ ሹፌር ርዝቁን እና ረዳቱን አስይዤዋለሁ በማለት መስክረዋል፡፡ ሌሎች ሁለት ካሊፋ የሚባሉት በጸጥታ ኃይሎች እየተፈለጉ እንደሚገኙ ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም 9ኛ ምስክር አቶ ኑራ መሀመድ ደግሞ በወቅቱ እራሱ በሸኔ ቡድን ተይዞ ታስሮ በነበረበት በቀን 27/03/2012 ዓ/ም ጃርደጋ የሚባል ጫካ ዉስጥ እያለ 7ኛ ተከሳሽ ነብዩ ባባከር፣5ኛ ተከሳሽ ዮሴፍ ጅራታ፣6ኛ ተከሳሽ ጋዲሳ ገለቱ፣ሽፋ ባባኪር እና ሚልክያስ የተባለ ሰዉ 14 የሚሆኑ ልጃገረዶችን ይዘዉ እንዳመጡ መስክረዋል፡፡

በመሆኑም ከቀረቡት ማስረጃዎች እና ከወንጀሉ ክብደት፤በኅብረተሰቡ ብሎም በሀገር ላይ ሊያሳድር የሚችለውን አሉታዊ ተፅዕኖ ጭምር ከግምት ውስጥ በማስገባት ሲመረምር ምንም እንኳን በአንድ ምስክር የተመሰከረባቸው ቢሆንም ከሌሎች ማስረጃዎች ጋር ሲገናዘቡ ተደጋጋፊ ማስረጃዎች ሆነው በመገኘታቸው እንዲሁም አመልካች በወንጀል ፈፃሚ ቡድኖች ውስጥ መገኘታቸው ስለተመሰከረባቸው እንደበቂ ማስረጃ በመውሰድ አመልካች ክሱን ከ5ኛ፣6ኛ፣7ኛ እና 8ኛ ተከሳሾች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1/ሀ)፣35፣38 እና በአዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 3/3 ስር ሊከላከሉ ይገባል በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡

አመልካች 4 መከላከያ ምስክር የቆጠሩ ቢሆንም ለመከላከያ ምስክሮቹ መጥሪያ ካደረሰ በኋላ ሁለቱ በጸጥታ ኃይሎች ስለተገደሉ ማቅረብ እንደማይችል፤3ኛዉም በዚሁ ምክንያት ሸሽቶ ስለጠፋ ማቅረብ እንዳልቻለ በመግለጽ 1 መከላከያ ምስክር ብቻ አቅርቦ አሰምቷል፡፡ምስክሩ የሚያስረዳለትም ጭብጥ " አመልካች ወንጀሉን ፈጸመ በተባለበት በቀን 24/03/2012 ዓ/ም፣ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል መንግሥት በቂለም ወለጋ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ዉስጥ ከጠዋት 3፡00 እስከ 11፡00 ሰዓት ባለዉ ጊዜ ተከሳሹ እና የመከላከያ ምስክሩ አብረዉ ድንጋይ ሲያወጡ የዋሉ መሆኑን ሥራዉን ሁለቱ ብቻ ሲሰሩ እንደነበር እና በእለቱ የጫኑት ድንጋይ እንዳልነበር፡፡” እንደሚመሰክርለት ገልጿል፡፡

መከላከያ ምስክሩ በሰጡት ምስክርነት ቃል ፡- በቀን 24/03/2012ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡00 ጀምሮ እስከ ቀኑ 11፡00 ድረስ ከአመልካች ጋር የግል ሥራችንን እየሠራን አብረን ድንጋይ ስናወጣ ውለናል፡፡ ከአመልካች ጋር ምሳ የበላነው የኔ ቤት ሲሆን ምሳውን የበላነውም ከቀኑ 7፡00 እስከ 7፡30 ሰዓት በነበረው ጊዜ ሲሆን 7፡30 ሰዓት ላይ ወደ ሥራችን ተመለስን፡፡በዚህም እለት እስከ ቀኑ 11፡00 ሰዓት ድረስ ከአመልካች ጋር ሳንለያይ አብረን ሥራ ስንሠራ ነበር፡፡ከአመልካች ጋር አብረን ሥራ ስንሠራ የዋልንበት ቦታ እና የእኔ ቤት በግምት የ05 ደቂቃ የእግር መንገድ የሚራራቅ ሲሆን የአመልካች ቤት ርቀት ግን ከሥራ ቦታችን በእግር ከ15 ደቂቃ በላይ ያስኬዳል፡፡ የምናወጣውን ድንጋይ ዩኒቨርሲቲና ባለሀብቶች እየመጡ ገዝተውን በሲኖ ትራክ አስጭነው ይወስዱ ነበር፡፡ይህንን ሥራ ከአመልካች ጋር ከ1 አመት በላይ አብረን ሰርተናል፡፡ አመልካች በዚህ ወንጀል ተጠርጥሮ የታሰረው ከ25/03/2012ዓ.ም ጀምሮ ነው፡፡ማኅበራችን የተመዘገበ ማኅበር አይደለም፡፡ነገር ግን ሥራውን ከአመልካች ጋር ቅዳሜና እሁድን ሳይጨምር በሳምንት ከ4 እስከ 5 ቀን እንሠራ ነበር በማለት መስክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 255390 ላይ በቀን 19/12/2014 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት በሰጠዉ ፍርድ -አመልካች በቀን 24/03/2012ዓ.ም በነበረው የተማሪዎች የጠለፋ ወንጀል ላይ ስለመሳተፉ በአንድ የዐቃቤ ሕግ ምስክር የተረጋጠበት ሲሆን የቀረቡት የሰነድ ማስረጃዎች ደግሞ ወንጀሎቹ መፈፀማቸውን በሚገባ ያሳያሉ፡፡አመልካች በመከላከያ ምስክርነት ያቀረበው አንድ ምስክር ቢሆንም የሁለቱ ምስክሮች ቃል በአንድነት ሲመዘኑ ስለወንጀሉ የመሰከረበት የዐቃቤ ሕግ ምስክር በዕለቱ አጋቾች አምልጦ ወደ ቤቱ ከገባ በኋላ ለፖሊስ አመልክቶ የነበረና በዕለቱ በቀን 24/03/2012ዓ.ም ከቀኑ 9፡00 ሰዓት ላይ ከ3ቱ ከሊፋዎች አንዱን እራሱ ምስክሩ ጠቁሞ በመከላከያ ሰራዊት ያስያዘው መሆኑን ያረጋገጠ ከመሆኑም በተጨማሪ፤ አመልካች በዚሁ ዕለት ከመከላከያ ምስክሬ ጋር ድንጋይ ስናወጣ የዋልን ቢሆንም የሸጥነው ድንጋይ አልነበረም ያለ ሲሆን የመከላከያ ምስክሩ ግን በተቃራኒው በዕለቱ ድንጋይ አውጥተው ለዩኒቨርሲቲው እና ለባለሀብቶች ሸጠውላቸው በሲኖ ትራክ ጭነው ሲያስወስዱ እንደዋሉና አመልካች በዚሁ ወንጀል ተጠርጥሮ በማግስቱ በቀን 25/03/2012ዓ.ም እንደተያዘ መስክሯል፡፡ በመሆኑም በእርግጥም በዕለቱ አመልካች እና የመከላከያ ምስክሩ አብረው ሲሰሩ ስለመዋላቸው ጥርጣሬን የሚፈጥር እንጂ ከጥርጣሬ በፀዳ መልኩ ያስረዳው ነገር ባለመኖሩ የዐቃቤ ሕግ ክስ እና ማስረጃ በማስተባበል ሊከላከል ያልቻለ መሆኑ ግንዛቤ ተወስዶበታል፡፡ ስለሆነም አመልካች የቀረበትን ክስ እና ማስረጃዎች በመከላከያ ምስክሮቹ አማካኝነት በማስተባበል ስላልተከላከለ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 22(1/ሀ)፣35፣38 እና ለአመልካች የተሻለ ጠቃሚ በሆነዉ በአዋጅ ቁጥር 1176/2012 አንቀጽ 3(1/ሐ) ስር ጥፋተኛ ነዉ ሲል ወስኗል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በመቀጠል የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት መርምሮ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሰረት ደረጃ በማዉጣት ደረጃዉን በከባድ ላይ በመመደብ መነሻ ቅጣት 14 ዓመት ጽኑ እስራት በመያዝ በእርከን 31 ላይ አሳርፏል፡፡ማክበጃ ምክንያትን በተመለከተም የወንጀል ድርጊቱ የተፈፀመው በጥላቻ፣መጥፎ ነገር ለማድረግ ወይንም ሰውን ለመጉዳት በፍፁም ፍቃደኝነት በመሆኑ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 84(1/ሀ) መሰረት እንዲሁም ከሸኔ ቡድን ጋር ቀድሞ በተደረገ ስምምነት የሽብር ወንጀል ለመፈፀም በተቋቋመ ቡድን ውስጥ በመስማማት የፈፀሙ በመሆኑ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 84(1/መ) መሰረት ሁለት የማክበጃ ምክንያቶች በመያዝ የእስራ ቅጣቱን ወደ እርከን 33 ከፍ አድርጎታል፡፡የቅጣት ማቅለያን በተመለከተም የወንጀል ሪከርድ አለመኖሩ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 82(1/ሀ) መሰረት የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 86 መሰረት በማኅበራዊ ዘርፍ ውስጥ በበጎ አድራጎት ተግባራት ሲሳተፉ የነበሩ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ ከተለያየ ተቋማት ያቀረቡ መሆኑን በመገንዘብ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 86 መሰረት እንዲሁም በችሎት ሲቀርቡ የሚያሳዩት ጠባይ መልካም የነበረ እና ይህም የሕግ አክባሪነት ባህሪን የተላበሱ መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 82/1 እና በወንጀል ሕግ አንቀፅ 86 መሰረት አራት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን በመያዝ ከእርከን 33 ወደ እርከን 29 ዝቅ እንዲል በማድረግ በ11 ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ በአብላጫ ድምጽ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 237503 ላይ በቀን 29/06/2015ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 195/1 መሰረት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

አመልካች በቀን 09/09/2015ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉ ከላይ በተመለከተዉ መሠረት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታዉ አጭር ይዘት፡- የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንድከላከል ብይን የሰጠው የወንጀሉ ክብደት፣በህብረተሰቡ ብሎም በአገር ላይ ሊያሳድር የሚችለውን ተጽዕኖ ጭምር ከግምት በማስገባት በሚል ነው፡፡በኢትዮጵያ የፍትህ ስርዓት ውስጥ በተለይም የወንጀል ፍትህ ስርዓትን በተመለከተ አጠቃላይ የወንጀል ሕግ መርሆችን፣ ዓለም አቀፍ ልማዳዊ አሰራር እና በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 141፣42(1/ሀ) ስር ከተገለጸው አገላለጽ አንጻር የወንጀሉን ክብደት፣ወንጀሉ በህብረተሰቡና በአገር ላይ የሚያደርሰውን ተጽዕኖ መሰረት በማድረግ የሚደረግ የማስረጃ ምዘና ስርዓት የለም፡፡በኢትዮጵያ ከጥርጣሬ የጸዳ የማስረጃ ምዘና ስርዓትን መከተል አለመከተላችንን በተመለከተ የሚያከራክር ቢሆንም በወንጀል ጉዳይ ላይ የምንከተለው የማስረጃ ምዘና ስርዓት የተሻለ ማስረዳት የሚባለውን የማስረጃ ምዘና ስርዓት እንዳልሆነ ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 141 እና 142(1/ሀ) ላይ መረዳት ይቻላል፡፡ፍርድ ቤቶች አንድን ተከሳሽ የቀረበበትን ክስ እንዲከላከል ብይን ለመስጠት ዐቃቤ ሕግ ክሱን በበቂ ማስረጃ ያስረዳው መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡ የዐቃቤ ሕግ ምስክሩ ወንጀሉ ተፈጸመ በተባለበት በቀን 24/03/2012 ዓ.ም በቦታው እንደነበረና እራሱም የግል ተበዳይ እንደነበረ ከገለጸ በኋላ በዕለቱ ስሟ ዘመድ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የምትባል ተማሪ እና የራሱን ልጅ ጨምሮ 7 የዩኒቨርስቲው ተማሪዎች እንደታገቱ፤ እገታው ሲፈጸም ከሊፋ የሚባሉ ሶስት ሰዎች እንደነበሩበት እና ከሶስቱ ከሊፋዎች አንዱን ከሊፋ በዕለቱ በግምት 9:00 ከቀኑ በጸጥታ አካላት እንዳስያዘው መስክሯል፡፡ይሁን እንጂ ዘመድ የምትባል ተማሪ ታገቱ የሚባሉ ተማሪዎች ውስጥ የምትገኝ ስለመሆኑ በዐቃቤ ሕግ ክስ አልተጠቀሰም፤ ከዩኒቨርስቲው በቀረበው የታገቱ ተማሪዎች ስም ዝርዝር ውስጥም ዘመድ የምትባል ተማሪ ስም አልተጠቀሰም፡፡እንዲሁም ድርጊቱን ከፈጸሙት አንዱን ከሊፋ በዕለቱ በጸጥታ አካላት አስይዤዋለሁ ቢልም በችሎት ሊያሳየኝ አልቻለም፡፡ይህም የስም መመሳሰል እንጂ እኔ በድርጊቱ ያልተሳተፍኩ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡እኔ የተያዝኩት በቀን 25/03/2012ዓ.ም እንጂ በቀን 24/03/2012ዓ.ም አይደለም፡፡ ሆኖ ዐቃቤ ሕግ አመልካች የተከሰስኩበትን ወንጀል መፈፀሜን በበቂ ማስረጃ ሳያስረዳና የጥርጣሬው ተጠቃሚ አመልካች ልሆን ሲገባ ክሱን እንዲከላከል ብይን መስጠቱ በወ/መ/ሥ/ሥ/ ሕግ ቁጥር 141 የተደነገገዉን እና በሰ/መ/ቁጥር 89676 የተሰጠዉን የሕግ ትርጉም የሚቃረን በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡

በተጨማሪም ተከሳሽ የቀረበበትን ክስ ከጥርጣሬ በጸዳ መልኩ መከላከል አለበት የሚል በአገራችንም ሆነ በሌሎች አገሮች የተለመደ የማስረጃ ምዘና ስርዓት የለም፡፡የቅጣት ውሳኔን በተመለከተም የወንጀሉን ማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮች መልሶ እንደቅጣት ማክበጃ መያዙ እና የወንጀሉን ደረጃ ለመመደብ እንደምክንያት የተጠቀመው ወንጀሉ ሆን ተብሎና ታስቦበት የፖሊቲካ ጥቅምን ለማግኘት የተፈጸመ እና የተፈጸመውም በተማሪዎች ላይ ነዉ በሚል ደረጃውንም ከፍተኛ በማለት መያዙ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው ተብሎ ይሻርልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ይህ የሚታለፍ ከሆነም የወንጀሉ ደረጃ ቀላል ተብሎ ተይዞልኝ ቅጣቱ ቀልሎ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቋል፡፡

ችሎቱ የሰበር አቤቱታዉን ከስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ጋር አገናዝቦ በመመርመር አመልካች የተከሰሰበትን ወንጀል እንዲከላከል እና ጥፋተኛ ተብሎ ሲወሰን በክሱ ላይ የተጠቀሰውን የወንጀል ድርጊት መፈፀሙን ዐቃቤ ሕግ ተቀባይነት ባለው በማስረጃ የማስረዳት ደረጃ ልክ ማስረዳቱ ተረጋግጦ መሆን አለመሆኑን፤ የአመልካች መከላከያ ማስረጃ የተመዘነበትን አግባብ የማስረጃ ምዘና፤ የማስረዳት ሸክምና ደረጃ ከሚመለከተው መሰረታዊ መርሆዎች አተገባበር አኳያ በሰ/መ/ቁጥር 45595፣ 64813 (በቅፅ12) ፣ 225975(ያልታተመ) እና በሌሎች መዛግብት ላይ ከተሰጠው የሕግ ትርጉም አንፃር ለመመርመር፤እንዲሁም የቅጣት ውሳኔ የተላለፈበት አግባብ በተለይም የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች አያያዝ ሕግን የተከተለ መሆን አለመሆኑን ተጠሪ ባለበት ለመመርመር መዝገቡን አስቀርቦ ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ አዝዟል፡፡

ተጠሪ በቀን 27/03/2016ዓ.ም በሰጡት መልስ - አመልካች ላይ የተሰማው የዐቃቤ ሕግ ምስክር አንድ መሆኑ በስር ፍርድ ቤትም የተገለፀ ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ የምስክሩን ቃል ሲመዝን ምንም እንኳን አንድ ምስክር ብቻ ቢሆንም በማለት ነገር ግን እንዴት ተቀባይነት ሊኖረው ቻለ የሚለውን በግልፅ አስቀምጧል፡፡ምስክሩ በወቅቱ ወንጀሉ ሲፈፀም አብሮ የነበረ፤አመልካችን በወቅቱ ያየው ስለመሆኑ እና

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ያስያዘውም እሱ ስለመሆኑ ከመግለፁም በላይ ስለአመልካቹ ማንነት በአካላዊ ሁኔታ በችሎት ጠቁሞ አሳይቷል፡፡ፍርድ ቤቱ ማስረጃውን ሲመዝን የወንጀሉን ክብደት እና አሉታዊ ተፅዕኖውን ከግምት ያስገባ መሆኑን መግለፁ አግባብነት ያለው ነው የሚል እምነት ባይኖረንም የተሰማው ምስክር ግን እምነት የሚጣልበት ነው፡፡የተሰማው ምስክር አንድ ብቻ መሆኑ ማስረጃውን ተቀባይነት እንዳይኖረው የሚያደርግበት የማስረጃ ምዘና አካሄድ የለም፡፡ከሌሎች አባሪ ማስረጃዎች ጋር ሲታይ የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ በአመልካች ላይ በሚገባ አስረድቷል፡፡ በስም የተጠቀሰችው ተማሪ በክሱ ላይ አልተገለፀችም የሚለውን በተመለከተ ሁሉም የተጠለፉት ተማሪዎች ማንነት ተረጋግጦ በክሱ ላይ ላይገለፅ ይችላል፡፡ በሌላም በኩል ከ2 በላይ ስም ያላቸው ሰዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ ታሳቢ ሊደረግ ይገባል፡፡ በመሰረታዊነትም ይህ የዐቃቤ ሕግን ክስ ለማስረዳት ከግንዛቤ ውስጥ ሊገባ የሚችል ጉዳይ አይደለም፡፡ምስክሩ ቃሉን ሲሰጥ በግልጽ እንዳስረዳው አብረው የተጠለፉ ተማሪዎችን በዕለቱ ያገኛቸው እንጅ ከዚያ በፊት እውቅና ያላቸው አይደሉም፡፡አመልካች የተያዘበትን ቀንም በተመለከተ ሕዳር 24 እና 25 የሚለው ምስክሩ አመልካችን ጠቁሞ ያስዘው ከመሆኑ አንጻር እምነት የሚጣልበት ምስክርነት ነው፡፡ይህ ባይሆን እንኳ ከጊዜው ርዝመት አንጻር የአንድ ቀን ልዩነት በመሰረታዊነት ሊነሳ የሚገባው ጉዳይ አይደለም፡፡አመልካች እንዲከላከል ብይን ከተሰጠ በኋላ አቅርቦ ያሰማው ምስክር ከአመልካች ጋር አንድ ላይ ድንጋይ ስናወጣ ነበር ያለ ሲሆን በዕለቱ ድንጋዩን ለዩኒቨርሲቲ እና ባለሀብቶች ገዝተው በመኪና እየጫኑ ወስደውታል በማለት የመሰከረ ቢሆንም አመልካች ያስያዘው ጭብጥ ግን በዕለቱ ድንጋይ ያልሸጡ እና ያልተጫነ መሆኑን ነው፡፡የመከላከያ ምስክሩ አንድ ከመሆኑ አንጻር ከሌላ መከላከያ ምስክር ቃል ጋር ማመሳከር ስለማይቻል አመልካች ባስያዘው ጭብጥ አግባብ የመከላከያ ምስክሩ ቃል አመልካች ካስያዘው ጭብጥ ጋር የሚቃረን በመሆኑ አመልካች ተከላክሏል ሊባል የሚችልበት ሁኔታ የለም፡፡ ከቅጣት ማክበጃ አያያዝ ጋር በተያያዘ ድርጊቱ የተፈፀመው በተማሪዎች ላይ መሆኑ እና ተላልፈው የተሰጡትም ለሸኔ የሽብር ቡድን መሆኑ እና የተማሪዎች ያሉበት ሁኔታ አለመታወቅ እና የቤተሰብ ጭንቀት ሲታይ የወንጀሉን አፈፃፀም ከባድ ያደርገዋል፡፡ ተማሪዎቹ ምን ሊገጥማቸው እንደሚችል እያወቁ ያደረጉት በመሆኑ ከባድ ተብሎ መወሰኑ የሚነቀፍ አይደለም፡፡በሌላም በኩል 2 ማክበጃ መያዙንም በተመለከተ የወንጀል ድርጊቱ የተፈፀመው ማንነትን መሰረት ባደረገ መልኩ ነው፡፡ይህ ደግሞ የሽብር ወንጀል ማቋቋሚያ አይደለም፡፡ሌላም በኩል ድርጊቱ የተፈፀመው ሆን ተብሎ በሚል የቀረበው አገላለፅ ወንጀል ተጎጂዎችን ማንነት እና ምን አይነት ጉዳት ሊደርስባቸው እንደሚችል እያወቁ ያደረጉት መሆኑን ለመግለፅ እንጅ የሽብር ወንጀሉ የተፈፀመው ሆን ተብሎ ነው የሚለውን ለማመላከት አይደለም፡፡ ከቅጣት አወሳሰን ጋር በተያያዘ በስር ፍርድ ቤት የተፈጸመ ስህተት የለም፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ፍርድ እና ውሳኔ በማጽናት ውሳኔ እንዲሰጥልን በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም የመልስ መልሱን በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

ከላይ አጠር ባለ መልኩ የተገለጸዉ በዚህ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና በስር ፍርድ ቤት የተሰጡ ውሳኔዎች እንዲሁም የግራ ቀኙን ክርክር የሚመለከት ሲሆን እኛም አስቀድሞ የተያዘዉን ጭብጥ ከግምት

በማስገባት አመልካች ክሱን እንዲከላከልና ጥፋተኛ ተብሎ እንዲቀጣ በመወሰኑ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የሕግ ስህተት መፈጸም አለመፈጸሙን እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

በአገራችን በተዘረጋዉ የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሥርዓት መሠረት ሕጉ-ወጥነቱና አስቀጪነቱ በሕግ የተደነገገዉን በማድረግ የሚፈጸም የወንጀል ድርጊትም ሆነ አል ድርጊት ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮችን በአንድነት በሚያሟላ አኳኋን ስለመፈጸሙ በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ በፍርድ ቤት የተረጋገጠበት ወንጀል ፈጻሚ በወንጀል ሕጉ ወይም አግባብነት ባለዉ ሌላ ሕግ የተደነገገዉን ቅጣት መቀጣት ይገባዋል፡፡ በዚህ አግባብ ማንኛዉም ሰው በወንጀል ደርጊት ተጠያቂ የሚሆነው የተከሰሰበትን ድርጊት ወንጀል አድርጎ በሚደነግገዉ ሕግ ላይ በተመለከተዉ መሠረት ድርጊቱን ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት መፈጸሙ በማስረጃ ሲረጋገጥ ነዉ፡፡ ስለሆነም በወንጀል ሕጉ ልዩ ድንጋጌዎችና በሌላ ልዩ ሕግ በተለየ ሆኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ተከሳሹ ጥፋተኛ ሆኖ እንዲቀጣ ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል ስለመፈጸሙ ዐቃቤ ሕግ ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች መሟላታቸዉን በሚያረጋግጥ አኳኋን አግባብነትና በሕግ ተቀባይነት ያለዉን ማስረጃ በማቅረብ ማስረዳት ይጠበቅበታል፡፡(በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 1፣2፣ 23፣ 58 እና 59 እንዲሁም የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 141 ፣ 142/1 እና 149 ስር የተደነገገዉ ይመለከቷል)፡፡

በሌላ በኩል የወንጀል ክስ የቀረበበት ሰዉ የወንጀል ድርጊት አለመፈጸሙ ወይም የወንጀል ሕጉ የወንጀል ተጠያቂነትን በሚያስከትለዉ ተካፋይነት ደረጃ በወንጀል አፈጻጸሙ ተካፋይ አለመሆኑ ሲረጋገጥ ከቀረበበት የወንጀል ክስ በነጻ የሚሰናበትበትን አግባብ በአገራችን የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡ ፍርድ ቤቶችም ክርክር ሲሰሙ፣ማስረጃ ሲመረምሩና ሲመዝኑ እንዲሁም ዳኝነት በተጠየቀበት ጉዳይ ላይ ዉሳኔ ሲሰጡ ከማንኛዉም ተጽዕኖ ነጻ በመሆንና ከሕግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ ሳይመሩ የወንጀል ሕጉን ግብ፣ ዓላማዎችና መርሆዎች ባከበረ እንዲሁም የተጎጂዉን፣የሕዝብና የመንግሥት መብትና ጥቅም ለማስከበር በሕግ ሥልጣን የተሰጠዉን ከሳሽ እና የተከሰሰዉን ሰዉ መብቶች በአግባቡ ባገናዘበ አኳኋን የቀረበላቸዉን የወንጀል ክስ፣ክርክር እና ማስረጃ አግባብነት ካለዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር አገናዝበዉ በመመርመር በገለልተኛነት እና በሙሉ ነጻነት የዳኝነት ተግባራቸዉን የማከናወን ግዴታ እና ኃላፊነት እንዳለባቸዉ በኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 9(1፣2፣ እና 4)፣13፣20፣37፣79(2 እና 3) ፣ከወንጀል ሕጉ ታላቅ ክፍል እና ከወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕጉ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች በተከሰሰበት 1ኛ ክስ ላይ አብረዉት ከተከሰሱት ሌሎች ተከሳሾች ጋር በመሆን አመልካች ፈጸመ የተባለዉ ወንጀል በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1/ሀ)፣35.38 እና የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 3/3 ስር የተደነገገዉን በመተላለፍ ከላይ ዝርዝሩ በተገለጸዉ አግባብ ሕዳር 24 እና 25 ቀን 2012 ዓ/ም በቄለም ወለጋ ዞን ሰዮ ወረዳ እና አንፍሎ ወረዳ ላይ በክሱ የተጠቀሱትን 16 የአማራ ክልል ተማሪዎችን በማገት ለኦነግ ሸነ አሸባሪ ቡድን የበላይ አመራሮች ለሆኑት ከላይ በስም

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ዉሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ለተጠቀሱትና ተለይተዉ ላልታወቁ አሸባሪዎች አሳልፎ የሰጠ በመሆኑ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን የሽብር ወንጀል ፈጽሟል በሚል ነዉ፡፡

ከፍ ሲል በተመለከተዉ መሠረት አመልካች የተከሰሰበትን ወንጀል እንዳልፈጸመ በመግለጽ ክዶ በመከራከሩ ዐቃቤ ሕግ በአዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 23 ስር ተቀባይነት አላቸዉ የተባሉ ማስረጃዎችን እና/ወይም ሌሎች አግባብነት ያላቸዉን ማስረጃዎች በማቅረብ ማስረዳት ይጠበቅበታል፡፡ እንዲያስረዳ የሚጠበቅበትም አመልካች በአዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 3/3 ስር እንደተደነገገዉ ፖለቲካዊ ወይም የአይዲዮለጂ ዓላማዉን ለማራመድ በማሰብ በመንግሥት ላይ ተጽእኖ ለማሳደር ወይም ሕብረተሰቡን ወይም የሕብረተሰቡን ክፍል ለማስፈራራት በማሰብ የወንጀሉ ድርጊት በሚሰጠዉ ዉጤት ሙሉ ተካፋይ በመሆንና ዉጤቱን የራሱ በማድረግ እገታ ወይም ጠለፋ በተማሪዎቹ ላይ መፈጸሙን ነዉ፡፡

ተጠሪ ከላይ ከተመለከተዉ አንጻር ለማስረዳት ካቀረባቸዉ 17 ምስክሮች ዉስጥ አመልካችን በተመለከተ የመሰከረዉ 1(አንድ) ምስክር ብቻ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ይህ 1(አንድ) ምስክር አመልካችን በተመለከተ የሰጡት ምስክርነት ቃል ይዘት እንደሆነ በስር ፍርድ ቤት ፍርድ ላይ የተመለከተዉ አመልካች ካሊፋ አብዱረህማን እና ናስር መሀመድ የሚባል 8ኛ ተከሳሽ ከሌሎች ካልታወቁ ሰዎች ጋር በመሆን በተማሪዎች እገታ ወንጀል ላይ መሳተፋን የሚገልጽ ነዉ፡፡በስር ፍርድ ቤት የፍርድ ሀተታ ላይ እንደተገለጸዉ እኚህ ምስክር ከተማሪዎቹ ጋር አብረዉ ታገተዉ የነበሩና በኋላም ከአጋቾቹ አምልጠዉ የወጡ መሆኑን ከማስረዳታቸዉም በተጨማሪ አመልካችን ጠቁመዉ ያስያዙት እርሳቸዉ እንደሆኑ አስረድተዋል፡፡ ምስክሩ በሰጡት ቃል አጋቾቹ ፊታቸዉ(ገጽታቸዉ) ተለይቶ እንዳይታወቅ ገጽታቸዉን ለመለወጥ ወይም ለመሸፈን የፈጸሙት ነገር መኖሩን ለይተዉ ስላልገለጹ እገታዉን የፈጸሙትን ሰዎች በመልክ ለመለየት የሚያስችል አጋጣሚ እንደነበራቸዉ ነዉ፡፡ይህንንም አጋጣሚ እንደተጠቀሙ በሚያሳይ መልኩ አመልካችን ጠቁመዉ ማስያዛቸዉን ገልጸዋል፡፡

ሆኖም ይህ ምስክር ከሊፋ በሚል የገለጹት ተከሳሽ የአሁን አመልካች መሆን አለመሆኑን ለይተዉ የሚያዉቁ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ በማሰብ የስር ፍርድ ቤት በችሎት የምስክርነት ቃላቸዉን ሲሰጡ ምስክሩ ከተከሳሾች መካከል አመልካችን እንዲለዩ ሲጠይቃቸዉ መለየት እንደማይችሉ ከመግለጻቸዉም በተጨማሪ ፀጉሩን፣መልኩን እና አካላዊ ገጽታዉን መሰረት አድርገዉ ሲገምቱ ካሊፋ(አመልካችን) ይመስላል በሚል ያሳዩት 5ኛ ተከሳሽ የሆነዉን ዮሰፍ ጅራታ እንደሆነ በፍርዱ ላይ ተመልክቷል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን እና በይግባኝ ሰሚነት የሚዳኙ ፍርድ ቤቶች በሕግ በተሰጣቸዉ ሥልጣን መሠረት የማስረጃ አቀራረብን፣ አግባብነትን፣ ተቀባይነትን እና ማስረጃ አቅርቦ አንድን ፍሬ ነገር የማስረዳት ሸክም የሚመለከቱ መርሆዎች (Principles of Production, relevancy, admissibility and burden of proof of evidence) አተገባበር በሚቃረን አኳኋን እንዲሁም የማስረጃ ምዘናን ወይም የማስረዳት ደረጃን

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

(standards of proof or  weight of evidence) የሚመለከቱ መሰረታዊ መርሆዎች በመጣስ የመጨረሻ ዉሳኔ መስጠታቸዉ በግልጽ ሲረጋገጥ፤ በተጨማሪም በአንድ ማስረጃ ይዘት ላይ በግልጽ የተመለከተዉን ወይም በምስክሮች ተመስክሮ የተረጋገጠዉን በአግባቡ ያላገናዘበ እና ዉሳኔ የሚሻዉ የፍሬ ነገር ጭብጥ መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ አስፈላጊ ለሆነ ማስረጃ ተገቢዉን ዋጋ ሳይሰጡ ዉሳኔ ሲሰጡ፤ እንዲሁም በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠዉን ነጥብ ከሕጉ ጋር ሳያገናዝቡ መወሰናቸዉ ሲረጋገጥ ሰበር ችሎት ማስረጃ ወደ መመዘን ዉስጥ ገብቷል ሊባል እንደማይቻል እና እንደመሰረታዊ የሕግ ስህተት ተቆጥሮ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚገባ መሰረታዊ የሕግ ስህተት እንደሆነ በሰ/መ/ቁጥር 113464 (ቅጽ 19)፣ 225975፣ 246157 እና 228017 (ያልታተሙ) መዛግብት ላይ ይህ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

በያዝነዉ አመልካች በተከሰሰበት በዚህ ወንጀል በዋና ወንጀል አድራጊነት ተሳትፎ አድርጓል በሚል እስከተከሰሰ ድረስ በቀጥታ ወይም በእጅ አዙር በእርግጥም ተሳትፎ የነበረዉ ስለመሆኑና የነበረዉንም ተሳትፎ ደረጃ ወይም አይነት ቢያንስ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 141 ስር ተመላክቶ በተደነገገዉ ልክ በቂና አሳማኝ ማስረጃ በማቅረብ ዐቃቤ ሕግ ማስረዳት ይጠበቅበታል፡፡ ዐቃቤ ሕግ በዚህ ልክ ማስረዳት ባልቻለበት ተፈጸመ የተባለዉ ወንጀል በሕብረተሰቡና በመንግሥት ላይ ጉዳት ከባድነት ወይም የወንጀሉን ክብደት ከግምት በማስገባትም ሆነ ተያያዥነት የሌላቸዉን ፍሬ ነገሮች መሠረት በማድረግ ተከሳሹ ክሱን እንዲከላከል ግዴታ መጣል የማስረጃ ምዘና ፣ የማስረዳት ደረጃ እና ሸክም የሚመለከቱ መሠረታዊ መርሆዎችን መጣስ ስለሚሆን ሊታረም የሚገባዉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ከዚህ ጋር በተያያዘ የዐቃቤ ሕግ ምስክር በአመልካች ላይ መሠከሩ የተባለዉ ሲታይ - ምስክሩ የምስክርነት ቃላቸዉን የሰጡት በቀን 17/09/2013 ዓ/ም እንደሆነ ከመዝገቡ የተመለከትን ሲሆን ምስክሩ አመልካችን በጸጥታ አካላት አስይዣዋለሁ ያሉበት ቀን ደግሞ በቀን 24/03/2012 ዓ/ም ነዉ፡፡የእገታዉ ወንጀል የተፈጸመበት ቀን ነዉ ተብሎ በክሱ የተገለጸዉ ቀን ደግሞ ሕዳር 24 እና 25 ቀን 2012 ዓ/ም ነዉ፡፡ምስክሩ በእገታዉ ቀን አመልካችን እንዳዩት በማስታወስ አመልካችን የፀጥታ አካላት እንዲይዙት አድርገዉ ከሆነ እና 1 ዓመት ከ6 ወር አካባቢ ቆይታ በኋላ ለምስክርነት ችሎት በቀረቡበት ጊዜ አመልካችን ከተከሳሾች መካከል ለይተዉ እንዲያሳዩ ሲጠየቁ መለየት እንደማይችሉ መግለጻቸዉም ሆነ በኋላም ሌላ ተከሳሽ ማሳየታቸዉ በእርግጥም ይህንን አመልካች ከአጋቾች ጋር የእገታዉን ወንጀል ሲፈጽም ምስክሩ አይተዋል ወይ የሚል ጥያቄ የሚያስነሳ ምስክርነት መስጠታቸዉን የሚያሳይ ነዉ፡፡

የስር ፍርድ ቤት የምስክሩን ቃል ሲመዝን ከላይ ለተመለከተዉ ጥያቄ ጭምር መልስ በሚሰጥ አኳኋን መመዘን ይኖርበታል፡፡እንዲሁም አመልካች በጸጥታ አካላት የተያዘዉ በቀን 25/03/2012 ዓ/ም እንደሆነ በተጠሪም የታመነ  ጉዳይ ነዉ፡፡ እኚህ የዐቃቤ ሕግ ምስክር ደግሞ አመልካችን በመከላከያ ሠራዊት ያስያዝኩት የእገታ ወንጀል በተፈጸመበት ዕለት በቀን 24/03/2012 ዓ/ም ነዉ በማለት መስክረዋል፡፡ ምስክሩ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ዉሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በዚህ መልኩ የሰጡት ምስክርነት ቃል ከነገሮቹ ክንዉን ሁኔታ አንጻር ሲታይ በቀላሉ የአንድ ቀን መሳሳት ጉዳይ ነዉ ተብሎ የሚታለፍ አይደለም።ምክንያቱም ምስክሩ የእገታ ወንጀሉ የተፈጸመበትን ቀን በትክክል መግለጽ ከቻሉ በእርግጥም ጠቁመዉ ያስያዙት የአሁን አመልካችን እንጂ ሌላ በተመሳሳይ ስም የሚጠራ ሰዉ ካልሆነ ወንጀሉ ከተፈጸመ ከ1 ቀን በኂላ በቀን 25/03/2012ዓ/ም አመልካችን ጠቁመዉ ማስያዝ እንደቻሉ የመሰከሩት እዉነት ቢሆን ኖሮ በአንድ ቀን ልዩነት የተፈጸሙትን ተግባራት በትክክል ለማስረዳት ይቸገራሉ የሚያስብል አሳማኝ ምክንያት የለም። ወይም ቀናቱን በጊዜ ቆይታ ብዛት በመርሳት ዘንግተዉታል ሊባል የሚቻልበት ሁኔታ የለም። በመሆኑም የዐቃቤ ሕግ ምስክር በችሎት አመልካችን በአካል ለይተዉ ማሳየት አለመቻላቸዉ እና አመልካች በጸጥታ አካላት የተያዘበት ቀን 25/03/2012 ዓ/ም ሆኖ እያለ ምስክሩ ካሊፋ የተባለዉን አጋች ጠቁሜ አስያዝኩኝ በቀን 24/03/2012 ዓ/ም ነዉ በማለት የገለጹት እንዲሁም ከሊፋ በሚል ስም የሚጠሩ ሌሎች ሁለት ሰዎች እንዳሉ ከተመሰከረዉ ጋር ተደምሮ ሲታይ አመልካች በእገታዉ ተሳተፈ በማለት የመሰከሩበት ሰዉ ሌላ ከሊፋ የሚባል ሰዉ ነዉ ብሎ እምነት ለመጣል የሚያስችል ምክንያታዊ ጥርጣሬ የሚያጭር እንጂ አመልካች በወንጀሉ ተሳትፎ ነበረዉ ብሎ ለመደምደም የሚያስችል አይደለም።

በሌላ በኩል ምስክሩ አመልካችን ለጸጥታ አካላት ጠቁመዉ አስይዘዋል ቢባል እንኳን በእገታዉ ተሳትፏል ያሉት ካሊፋ አመልካች ቢሆን ኖሮ አጭር በሚባል ጊዜ ዉስጥ ችሎት ቀርበዉ የምስክርነት ቃላቸዉን ሲሰጡ ችሎት ዉስጥ ከነበሩ ተከሳሾች መካከል አመልካችን ለይተዉ ለችሎቱ ለማሳየት የሚያስቸግራቸዉ ሌላ በቂ ምክንያት ስለመኖሩ ተገልጾ የቀረበ ክርክርም ሆነ ማስረጃ የለም። በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት እነዚህን ምስክርነት ቃላት ጨምሮ ለአጠቃላይ ምስክርነት ቃሉ ተገቢዉን ዋጋ በመስጠት መመዘን ሲገባዉ ምስክሩ አመልካች ከአጋቾቹ ጋር አብሮ የእገታዉን ወንጀል ፈጽሟል፤በኂላም ጠቁሜ አስይዤዋለሁ በማለት የመሰከሩትን ብቻ በተናጠል በመመልከትና ትልቅ ዋጋ በመስጠት የምስክርነት ቃሉን ከእነ ሙሉ ይዘቱ አለመመዘኑን ተገንዝበናል። እንዲሁም ማስረጃ ሲመዘን ከግምት ሊገባ የማይገባዉን *"ወንጀሉ በሕብረተሰቡ ብሎም በአገር ላይ ሊያሳድር የሚችለዉ አሉታዊ ተጽእኖ ከፍተኛ ነዉ "* የሚል ፍሬ ነገር ከግምት በማስገባት ዉሳኔ መስጠቱ የዳኝነት ገለልተኝነት እና ነጻነት መርሆዎችን በአግባቡ ተግባራዊ አለማድረጉን የሚያሳይ ነዉ። ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት አመልካች ተላልፏል ተብሎ በክሱ ላይ የተጠቀሰበት የሕግ ድንጋጌዎችን መስፈርት በሚያሟላ አኳኋን በወንጀል አፈጻጸሙ ተካፋይ ስለመሆኑ ባለተረጋገጠበት አመልካች ክሱን እንዲከላከል ማዘዙ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 23/2 ስር የተደነገገዉን የወንጀል ሕግ መሠረታዊ መርህ የሚጥስ ፤የማስረጃ ምዘና መርህ አተገባበር ጉድለት የተፈጸመበት፣ በወ/መ/ሥ/ሥ/ ሕግ ቁጥር 141 ስር የተደነገገዉን የማስረጃ ምዘና ደረጃ ያልተከተለ፣ እንዲሁም በሕገ መንግሥቱ ጥበቃ የተደረገለትን የዳኝነት ገለልተኝነት እና ነጻነት መርሆዎችን የሚሸራርፍ የክርክር አመራርና ዉሳኔ በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነዉ ብለናል።

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ከላይ የተመለከተዉ በስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ላይ የታየዉ ጉድለት እንደተጠበቀ ሆኖ አመልካች ክሱን እንዲከላከል ከታዘዘ በኂላም ቢሆን የስር ፍርድ ቤት አመልካች ባቀረበዉ መከላከያ ምስክር ወንጀሉን ፈጸመ በተባለበት ቀን ከምስክሩ ጋር ድንጋይ እያወጣ እንደዋለ እና ወንጀል ተፈጸመ በተባለበት ስፍራ እንዳልነበር እንዳስመሰከረ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ያሳያል፡፡የስር ፍርድ ቤት አመልካች በማስተባበል አልተከላከለም የሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰዉ አመልካች ባስመዘገበዉ ጭብጥ ላይ በእለቱ ድንጋይ እንዳልሸጡ በተለጸበት መከላከያ ምስክሩ ደግሞ በእለቱ ድንጋይ ሸጠናል በማለት መመስከሩ *ጥርጣሬን የሚፈጥር እንጂ ከጥርጣሬ በጸዳ መልኩ በማስረዳት አልተከላከለለትም* የሚል ምክንያት በመጥቀስ ነዉ፡፡ የዚህን ምክንያት ተገቢነትና ማስረጃዉ የተመዘነበት አግባብ ተገቢ መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡ ይህም ከወንጀል ክርክር ማስረጃ ምዘና መርህ አተገባበር፣በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 149/1 ስለፍርድ አጻጻፍና ይዘት ከተደነገገዉ እንዲሁም በዳኝነት ሥራ አፈጻጸም ዳብሮ ተቀባይነት ካገኘዉ የወንጀል ክስ ክርክር ፍርድ አሰጣጥ አንጻር መታየት ይኖርበታል፡፡ በዚህ መሠረት በወንጀል የተከሰሰ ሰዉ የተከሰሰበትን ወንጀል ስለመፈጸሙ ከላይ በተመለከተዉ መሠረት ዐቃቤ ሕግ አግባብነት እና በሕግ ተቀባይነት ያለዉን ማስረጃ በማቅረብ ማስረዳቱ ተረጋግጦ ተከሳሹ ክሱን እንዲከላከል ታዝዞ መከላከያ ማስረጃዉን አቅርቦ ካሰማ በኂላ ፍርድ ቤቶች በግራ ቀኙ የቀረቡትን ማስረጃዎች መርምረዉና መዝነዉ የተቀበሉበትንና ያልተቀበሉበትን ምክንያት በፍርዱ ላይ አስፍረዉ ተከሳሹ በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ የተመሰከረበትን ወንጀል አልፈጸመም ወይም በወንጀሉ ተሳትፎ አልነበረዉም ብሎ ለማመን በሚያስችል ደረጃ ምክንያታዊ ጥርጣሬ ዉስጥ በመክተት ማስረዳቱን በማረጋገጥ ተገቢዉን ፍርድ መስጠት ይገባቸዋል፡፡ ተከሳሽ በዚህ ልክ አስረድቶ እያለ የስር ፍርድ ቤት በዉሳኔዉ ላይ በገለጸዉ መሠረት *"ተከሳሹ ከጥርጣሬ በጸዳ መልኩ ወንጀል አለመፈጸሙን አላስረዳም"* በሚል ጥፋተኛ የሚደረግበት የማስረጃ ምዘና መርህ የለም፡፡

ሲጠቃለል አመልካች በተከሰሰበት የወንጀል ድርጊት ተሳትፎ እንደነበረዉ ዐቃቤ ሕግ በበቂ ሁኔታ በማስረጃ ባላስረዳበት አመልካች ክሱን እንዲከላከል ማዘዙም ሆነ መሆኑ የስር ፍርድ ቤት አመልካች *ከጥርጣሬ በጸዳ መልኩ ወንጀል አለመፈጸሙን አላስረዳም* በማለት አመልካችን ጥፋተኛ ነዉ በማለት ቅጣት መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ እያለ ይህንን ስህተት ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት አለማረሙ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሀ፣ለ እና ሸ) እና 10(1/ለ) መሠረት ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## **ዉ ሳ ኔ**

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 255390 ላይ በቀን 19/12/2014ዓ.ም አመልካችን በተመለከተ የሰጠዉ የጥፋተኝነት ፍርድ እና በቀን 10/02/2015ዓ/ም የሰጠዉ የቅጣት ዉሳኔ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 237503 ላይ በቀን

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

29/06/2015ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 መሰረት ተሽረዋል፡፡

2. በአመልካች ላይ የተላለፈዉ የጥፋተኝነት ፍርድም ሆነ የቅጣት ዉሳኔ ተሽሮ አመልካች በነጻ እንዲሰናበት ተወስኗል፡፡

## ትዕዛዝ

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ እንዲያዉቀዉ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ለግራ ቀኙም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. በዚህ የፍርድ ዉሳኔ መሠረት እንዲፈጽም የዉሳኔዉ ግልባጭ አመልካች ታስሮ ለሚገኝበት ማረሚያ ቤት ይጻፍ፡፡
3. የስር ፍርድ ቤት መዝገብ ይመለስ፡፡መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
## የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ.ቁ/247117

ጥቅምት 06 ቀን 2017 ዓ.ም

**ዳኞች፡-**ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻዉ አዳነ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሠናይት አድነዉ

ሀፊዝ አባጀማል

**አመልካች፡-** ተሻለ ወ/ገብርኤል - ቀርበዋል

**ተጠሪዎች፡-** 1. ወ/ሮ ላቀች ካሳ በየነ

2. ወ/ሮ ቡልኬ ባሳ ዙላ } አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን፣ የአሁን አመልካች በተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት ክስ እንደ ባልና ሚስት አብረዉ ሲኖሩ በነበረበት ወቅት በጋራ ያፈሩትን ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት 1ኛ ተጠሪ መስከረም 20 ቀን 2012 ዓ.ም በተደረገ ዉል ለ2ኛ ተጠሪ በስጦታ ማስተላለፋቸዉን ጠቅሰዉ የስጦታ ዉሉ እንዲፈርስ የጠየቁትን ዳኝነት መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡

ተጠሪዎች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን በማስቀደም በየበኩላቸዉ መልስ አቅርበዋል፡፡ በዚህም መሠረት 1ኛ ተጠሪ ከአመልካች ጋር እንደባልና ሚስት አብረዉ እንዳልኖሩ

**ማስታወሻ፡** - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

እና ልጃቸዉም የተወለደችዉ በነበራቸዉ የፍቅር ግንኙነት መሆኑን፣ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት 2ኛ ተጠሪ ቤት እንዲገዛላቸዉ በላኩት ገንዘብ በ1ኛ ተጠሪ ስም የተገዛ መሆኑንና ይህ ሲሆን አመልካች ምስክር በመሆን በዉልና ማስረጃ ጽ/ቤት ቀርበዉ በሽያጭ ዉሉ ላይ መፈረማቸዉን፣ ይህን ቤት እንዲያስረክቧቸዉ 2ኛ ተጠሪ ባቀረቡት ክስ መነሻነት በአፈፃፀም ያስረክቧቸዉ መሆኑንና የስጦታ ዉል የተደረገዉም ስመ ሀብቱ በሽያጭ ወይም በስጦታ ካልሆነ በቀር ስመ ሀብት ሊዛወር እንደማይችል በክ/ከተማዉ የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ክፍል ስለተገለጸላቸዉ እንጂ ንብረት ለማሸሸ አለመሆኑን ጠቅሰዉ ክሱ ዉድቅ ይደረግ ዘንድ መልስ ሰጥተዋል፡፡ 2ኛ ተጠሪም በሰጡት መልስ ከሞላ ጎደል ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ተመሳሳይ ይዘት ያለዉ ክርክር አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ፣ ምንም እንኳ አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር እንደባልና ሚስት የኖሩና ዘመዶቻቸዉና ባልና ሚስት ናቸዉ ብሎ የሚገምት መሆኑን ያስረዱ ቢሆንም፣ 1ኛ ተጠሪ በበኩላቸዉ ከአመልካች ጋር እንደ ባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት ዉስጥ ያልነበሩ መሆናቸዉን በማስረዳት አስተባብለዋል በሚል የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ በመድረስ የአመልካችን ክስ ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ዉሳኔ ባለመስማማት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም፣ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱም የይግባኝ መዝገቡን አስቀርቦ ከመረመረ በኋላ የስር ፍርድ ቤቱን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም በዚሁ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካች ግንቦት 01 ቀን 2015 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚሉባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር ታርሞ እንዲወሰንላቸዉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የሰበር አቤቱታቸዉ መሠረታዊ ይዘትም በአጭሩ አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር የነበረኝን የእንደባልና ሚስት ግንኙነት በእጅግ አብላጫ ማስረጃ ያረጋገጥኩ ሆኖ እያለ ባቀረቡት የሰዉ ምስክሮች አላረጋገጠም ተብሎ የተሰጠ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ነዉ የሚል ነዉ፡፡

የሰበር አቤቱታዉ በሰበር ችሎት ተመርምሮም አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር እንደ ባልና ሚስት የመኖር ግንኙነት አስመልክቶ እንዲቀርብ ተጠይቆ ከቀረቡት ማስረጃዎች አንፃር የስር ፍርድ ቤት እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት አልተረጋገጠም በማለት የሰጠዉን ዉሳኔ አግባብ ግራ ቀኝ በተገኙበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል ተብሏል፡፡ በዚህም መሠረት ተጠሪዎች የካቲት 08 ቀን 2016 ዓ.ም በጋራ አዘጋጅተዉ ባቀረቡት መልስ ከማስረጃ ጋር በተያያዘ አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለዉም የሚሉባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር አቤቱታዉ ዉድቅ ተደርጎ እንዲወሰንላቸዉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም የካቲት 19 ቀን 2016 ዓ.ም ጽፈዉ ባቀረቡት የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸዉን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉን ሲመስል፣ ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት በሆነዉ ዉሳኔ ላይ የተፈጸመ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉም መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደሚቻለዉ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ለጠየቁት የስጦታ ዉል ይፍረስልኝ ዳኝነት መሠረት ያደረጉት ቤቱ በ1ኛ ተጠሪ ስም ተመዝግቦ የነበረ ቢሆንም እንደባልና ሚስት በጋራ በሚኖሩበት ወቅት የተፈራ መሆኑን ሲሆን፣ 1ኛ ተጠሪ በበኩላቸዉ በግራ ቀኛቸዉ መካከል እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት አለመኖሩን ጠቅሰዉ መከራከራቸዉን ነዉ፡፡ አመልካች ለክርክሩ መነሻ በሆነዉ ቤት ላይ ድርሻ አለኝ ሲሉ መሠረት ያደረጉት ከ1ኛ ተጠሪ ጋር እንደባልና ሚስት አብሮ መኖራቸዉን በመሆኑ እና በአንፃሩ 1ኛ ተጠሪ ይህን ፍሬ ነገር ክደዉ የተከራከሩ ከመሆኑ አኳያ በጉዳዩ ላይ ፍትሐዊ ዉሳኔ ለመስጠት ይቻል ዘንድ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 246(1) መሠረት በጭብጥነት በመያዝ በማስረጃ መጣራት የሚገባዉ መሠረታዊ ነጥብ በአመልካች እና በ1ኛ ተጠሪ መካከል እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት መኖር አለመኖሩ ነዉ፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ የስር ፍርድ ቤትም ይህንኑ በጭብጥነት በመያዝ የግራ ቀኝ ምስክሮችን ሰምቷል፡፡ ግራ ቀኛቸዉ ያቀረቧቸዉ ምስክሮች የሰጡትን የምስክርነት ቃል መዝኖም፣ 1ኛ ተጠሪ ያቀረቧቸዉ ምስክሮች በፌዴራል የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 99(1) እና (2) ላይ በተመለከተዉ አግባብ በግራ መካከል እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት ያልነበረ ስለመሆኑ ከአመልካች ምስክሮች በተሻለ ሁኔታ አስረድተዋል ከሚል የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተዉ እና ማስረጃን መዝኖ ፍሬ ነገርን የማጣራት ስልጣን ያለዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በስር ፍርድ ቤት የቀረቡትን የግራ ቀኝ ምስክሮችን በድጋሚ በመመርመር እና በመመዘን በተመሳሳይ የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ ሁለቱም ፍርድ ቤቶች የግራ ቀኝን ምስክሮች መዝነዉ በዚህ የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ ሲደርሱ የፈጸሙት የማስረጃ አቀባበል እና የምዘና መርህ ስህተት ስለመፈጸማቸዉ የዉሳኔዎቹ ይዘት አያሳይም፡፡

በሌላም በኩል በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ) ላይ በግልጽ እንደተመለከተዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉን ዉሳኔዎች በማረም ላይ የተገደበ ነዉ፡፡ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 በትርጉም ክፍል አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለዉ አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን፣ ህግ ያላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉን ህግ የሚጠቅስ፣ ለክርክሩ አግባብነት ያለዉ ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለዉ ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ ሲሆን፣ በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ዉድቅ በማድረግ ሲወሰን፣ በፍርድ አፈፃፀም ሂደት ከዋናዉ ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትዕዛዝ የተሰጠበት ሲሆን፣ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተሰጠ ዉሳኔ ሲሆን፣ የአስተዳደር አካል ወይም ተቋም ከህግ ዉጭ የሰጠዉ ዉሳኔ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ በመቃረን የተወሰነ ሲሆን ነዉ፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በሚል የሰበር አቤቱታ ሲቀርብለት ለአቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ ጉዳይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ ከላይ በዝርዝር ከተመለከቱት ሁኔታዎች ዉስጥ

ማስ ታወሻ፡ - ይህ የ ሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነ ድ ለ ጥና ትና ምር ምር ሥራ ወይምለ ግንዛ ቤ እን ጂ

ለፍርድ አ ፈጻ ጸ ምዓላ ማአ ያገ ለግልም!

ቢያንስ አንዱን ያሟላ ሆኖ በዉጤቱም ጉልህ የሆነ የፍትሕ መጓደል የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ ከላይ ከተመለከተዉ የአዋጁ ድጋጌዎች ይዘት የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡

ከዚህ አንፃር የተያዘዉን ጉዳይ ስንመለከት የአመልካች ክስ ዉድቅ በማድረግ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በጸናዉ ዉሳኔ ላይ የተፈጸመ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ዉሳኔ</u>**

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 119636 ላይ ሐምሌ 28 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 295886 ላይ የካቲት ፩27 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጡት ዉሳኔ በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1) መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሠ/መ/ቁጥር 247213

ጥቅምት 05ቀን 2017 ዓ/ም

ዳኞች ፡- ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ብርሃኑ መንግሥቱ

ማርታ ተካ

አመልካች - ሃጂ አወል ሱሌማን

ተጠሪ -የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል መንግሥት ፍትሕ ቢሮ - ዐቃቤ ሕግ / አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ሀሰተኛ ሰነድ በማዘጋጀት፣በመፍጠር ወይም በመገልገል የወንጀል ክስ ሲቀርብ ሰነዱ ሀሰተኛ አይደለም የሚል ክርክር ሲቀርብ ሰነዱ ሀሰተኛ መሆን አለመሆኑ የሚረጋገጥበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት በካፋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ በአመልካች ላይ ፡- አመልካች የማይገባውን ጥቅም ለማግኘት እና ተበዳይ ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ በጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሸሪአ ችሎት በቁጥር 06135/2002 በቀን 22/08/13ዓ.ም ከድንቅነሽ በቀለ ጋር በሀሰት ኒካ ያሰረ በማስመሰል እና ተበዳይ ድንቅነሽ በቀለን ወደ እስልምና እምነት በመቀየር ስሚን ሀያት በቀለ በሚል ሀሰተኛ የምስክር ወረቀት በማዘጋጀት ለገዋታ ወረዳ ፍ/ቤት ለባል እና ሚስት ክርክር እንዲጠቀመው ለማድረግ የጋብቻ ሰነድ በማቅረብ ተበዳይ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ወ/ሮ ድንቅነሽ በቀለ ላይ ጉዳት ያደረሰ በመሆኑ የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ የወጣውን አዋጅ ቁጥር 881/07 አንቀጽ 23(1/ሀ) ስር የተደነገገውን ድንጋጌ ተላልፎ ሀሰተኛ ሰነድ ፈጥሯል የሚል የወንጀል ክስ መስርቶበታል፡፡

አመልካች የክስ ማመልከቻው እንዲደርሰዉ ተደርጎ ተነቦለት መቃወሚያ ያቀረበ ቢሆንም ያቀረበዉ መቃወሚያ ውድቅ በመደረጉ ወንጀሉን አልፈጸምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ክዶ ተከራክሯል፡፡ዓቃቤ ሕግ ምስክሯም በሰጡት የምስክርነት ቃል አመልካች በጋዋታ ፍርድ ቤት እርሳቸውን ሚስቴ ናት በማለት የባል እና የሚስት ፍቺ ጥያቄ እና የንብረት ክፍፍል ጥያቄ ጋር ማስረጃዉን አቅርበዉ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል በማለት መስክረዋል፡፡ይህንን ተከትሎ ፍርድ ቤቱ አመልካች ክሱን እንዲከላከል አዝዞ አቅርቦ ባሰማዉ መከላከያ ምስክር በሰጡት የምስክርነት ቃል አመልካች እና ወ/ሮ ድንቅነሽ በቀለ ባል እና ሚስት መሆናቸውን የሚያውቁ መሆኑን፤በተፈጠረው አለመግባባት ተኮራርፈው እያሉ ወ/ሮ ድንቅነሽ በቀለ ቀደም ሲል ይከተሉ የነበሩትን የእስልምና ሀይማኖት ወደ ክርስትና ሀይማኖት መቀየራቸውን የሚያውቁ መሆኑን፤በቀን 25/11/2002 ዓ.ም ወ/ሮ ወ/ሮ ድንቅነሽ ወደ እስልምና ሀይማኖት እመለሳለሁ ብለው ከአመልካች ጋር ጅማ ዞን ሄደው ሀያት በቀለ በሚል ስም ተቀይሮ ከዚያ በኋላ አብረው መቆታቸውን፤ አመልካችም በቀን 22/3/2013ዓ.ም የጋብቻ ማስረጃ ጅማ ሄደው ማምጣታቸውን የሚያውቁ መሆኑን፤ይህንንም እስከ ጅማ አብረው ሄደው የተመለከቱ መሆኑን መስክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 21417 ላይ ማስረጃዎችን መርምሮ በቀን 09/06/2015ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ ዐቃቤ ሕግ አመልካች ሀሰተኛ የጋብቻ ሰነድ አዘጋጅቷል በማለት ክስ አቅርቦ ያስረዳውን አመልካች መፍረስ የሚችለው ሰነዱ ሕጋዊ እና ከጂማ ዞን ከፍተኛ ሸሪዓ ችሎት የተሰጠ መሆኑን የሚገልፅ ሰነድ በማቅረብ እንጂ በሰው የምስክርነት ቃል ብቻ ጋብቻ አለ ሰነድም አለ በማለት ማስተባል የሚቻል አይሆንም፡፡እንዲሁም ፍርድ ቤቱ ለትክለኛ ፍርድ ይጠቅማል በሚል ብይን ከመስጠቱ በፊት ሰነዱ በጅማ ዞን ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት መኖሩን በተመለከተ ለማጣራት ትዕዛዝ ሰጥቶ ሸሪዓ ፍርድ ቤቱ ሰነዱ እንዳልተገኘ ገልጿል፡፡በመሆኑም ሰነዱ በአመልካች የተዘጋጀ እንጂ ሕጋዊነቱን ሊረጋግጥ ሥላልቻለ አመልካች የተከሰሰበትን ድንጋጌ ተላልፎ የተገኘ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 23(1/ሀ) ስር ጥፋተኛ ነዉ ሲል ወስኗል፡፡ ይህንን ተከትሎም የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት መርምሮ አመልካች በ1 ዓመት ከ8 ወር ጽኑ እስራት እና በብር 2000(ሁለት ሺህ) እንዲቀጣ ወስኗል፡፡

አመልካችም በዉሳኔዉ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ ተጠሪን ሳይጠራ በመ/ቁጥር 18015 ላይ በቀን 14/07/2015ዓ.ም በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 195/1 መሰረት በሠጠዉ ትዕዛዝ ሠርዞበታል፡፡በመቀጠልም አመልካች የሰበር አቤቱታዉን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ቢሆንም ችሎቱ በመ/ቁጥር 14341 ላይ በቀን 18/08/2015ዓ.ም በሠጠዉ ትእዛዝ የሕግ ስህተት አልተፈጸመም በሚል ሠርዞበታል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አመልካች በቀን 11/09/2015ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉ ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታዉ ይዘት በአጭሩ፡- የስር ፍርድ ቤት ለወንጀል ክሱ ምክንያት የሆነውን የጋብቻ የምስክር ወረቀት መመርመር የነበረበት ሰነዱን ያዘጋጀው አመልካች ነው? ወይስ የጂማ ዞን ሸሪዓ ፍርድ ቤት?፤አመልካች ለባል እና ሚስት ክርክር ያቀረበው ሰነድ በማስመሰል የተዘጋጀው ሀሰተኛ የጋብቻ የምስክር ወረቀት ነው? ወይስ ትክክለኛ የጋብቻ ምስክር ወረቀት? የሚሉትን ጭብጦችን መሆን ነበረበት፡፡እነዚህ ጭብጦች ሊረጋገጡ የሚችሉት ደግሞ በጋብቻ የምስክር ወረቀት ላይ ያረፈው ፊርማ እና ማህተም በፎረንሲክ ባለሙያ ተመርምሮ ሲረጋገጥ ነው፡፡ የባለሙያ ማረጋገጫ በሌለበት ከጅማ ዞን ሸሪዓ ፍርድ ቤት የተፃፈው ማብራሪያ ባልና ሚስቱ ኒካ በማሰር ጋብቻ ስለመፈፀማቸው በስማቸው ተመዝግቦ የሚገኝ መዝገብ ለማግኘት አልቻልንም የሚል ሲሆን ይህን ደብዳቤ ተቀብሎ አመልካች ሀሰተኛ የጋብቻ የምስክር ወረቀት አዘጋጅቷል ማለቱ የወንጀል ሕግን ማስረጃ የመመዘን መርህ የጣሰ በግምት የተሰጠ ውሳኔ ነው፡፡የጋብቻ ማስረጃው የጅማ ዞን ሸሪዓ ፍርድ ቤት ማህተም፣የፍርድ ቤቱ ሎጎ፣የፍርድ ቤቱ ዳኛ ፊርማና ስም ያለበት ሆኖ እያለ ሰነዱን ለመመርመር ብቃት ያለው አካል የሰጠው የሙያ ምርመራ ውጤት ሳይመጣ ዉሳኔ መሠጠቱ ስህተት ነዉ፡፡ሰነዱ ሀሰተኛ መሆን አለመሆኑ ሊረጋገጥ የሚችለው በባለሙያ ምርመራ እንጂ በፍርድ ቤት ውስጥ መዝገብ ተፈልጎ በመታጣቱ ሊሆን አይገባም፡፡ እነዚህ ማህተም፣ሎጎ፣የዳኛ ፊርማና ስም በሀሰት ተቀነባብሮ የተዘጋጀ ነው ለማለት ቀርቶ ለጥርጣሬ የሚያበቃ አንዳችም ምክንያት የለም፡፡ በአመልካች ላይ ተጠቅሶ የቀረበ ለክርክሩ መሰረት የሆነው የሕግ ድንጋጌ የአመልካችን ድርጊት በፍፁም የማያሳይ እና የአመልካች የወንጀል ድርጊት ከጥርጣሬ ዉጭ ባልተረጋገጠበት የተሰጠ ውሳኔ የማስረጃ ምዘና መርህ የሚጥስ ስለሆነ ሊታረም የሚገባዉ ስህተት ስለሆነ ሊሻርና አመልካች በነፃ ልሰናበት ይገባል በማለት አመልክቷል፡፡

ችሎቱ አቤቱታዉን መርምሮ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ከጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሸሪአ ችሎት ያቀረቡትን የኒካ ወረቀት በተመለከተ የጅማ ዞን ከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤቱ ተጠይቆ በሰጠው ምላሽ "ባል እና ሚስቱ ኒካ በማሰር ጋብቻ ስለመፈፀማቸው በስማቸው ተመዝግቦ የሚገኝ መዝገብ ለማግኘት አልቻልንም" ማለቱ አመልካች ሀሰተኛ ሰነድ ፈጥረዋል ሊያስብል ይችላል ወይ? የጋብቻ ምስክር ወረቀቱ በአመልካች እጅ መገኘቱ ብቻ አመልካችን ሀሰተኛ ሰነድ ፈጥረዋል ሊያስብል ይችላል ወይ? ድርጊቱስ ሀሰተኛ ሰነድ መፍጠር ወይስ ሀሰተኛ ሰነድ መገልገል ነው የሚሉትን ነጥቦች ከወንጀል ሕግ አንቀፅ 23/2 ድንጋጌ፣ከአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 23 ድንጋጌ እንዲሁም በሰ/መ/ቁጥር 89676 (ቅፅ 17) ላይ ከተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም አንፃር እንዲመረመር ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ አዝዟል፡፡

ተጠሪ በቀን 04/01/2016 ዓ.ም የተጻፈ መልስ በማቅረብ፡-አመልካች ሀሰተኛ የጋብቻ ምስክር ወረቀት በማዘጋጀት ለባል እና ሚስት ክርክር እንዲጠቀመው በማድረግ ተበዳይ ላይ ጉዳት ስለማድረሱ በስር ፍ/ቤት የተደረገ የፍሬ ነገር ክርክር ነው፡፡አመልካች በዓቃቤ ሕግ የቀረቡትን የሰው እና የሠነድ ማስረጃዎች

ማስተባበል አልቻሉም፡፡የኒካ የምስክር ወረቀት ሰጥቷል የተባለው ጅማ ዞን ሸሪዓ ችሎት ከአንድም ሁለት ጊዜ የጋብቻ የምስክር ወረቀቱ በተቋሙ ውስጥ ተመዝግቦ የማይገኝ ስለመሆኑ በሰነድ ያረጋገጠ ሲሆን ተበዳይም በችሎት ቀርባ ከአመልካች ጋር ኒካ አለማሰሯንና የጋብቻ የምስክር ወረቀት አለመቀበላቸውን ግልጻለች፡፡በአንፃሩ አመልካች ይህን ማስተባበል አልቻለም፡፡እንዲሁም አመልካች ሰነዱን ይዘው መገኘት ብቻ ሳይሆን ሰነዱን ለባል እና ሚስት ክርክር እንዲረዳቸው የሠነድ ማስረጃ አድርገው ስለማቅረቡ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡አመልካች ሀሰተኛ ሰነድ ያለመፍጠሩን በተመለከተ በተቃሪኒ ማስረጃ ባለማስተባበሉ በስር ፍርድ ቤት ጥፋተኛ ተብሎ የቅጣት ውሳኔ መተላለፉ ተገቢነት ያለው ነው፡፡ ከውጤት እና ከቅጣት አንፃር የአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 23/3 እና አንቀፅ 23/1 ላይ የተደነገገዉ ቅጣት ተመሳሳይ በመሆኑ በስር ፍርድ ቤት የተላለፈው የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔ ተገቢነት ያለው ነው፡፡በተጨማሪ አመልካች የፈፀመው ድርጊት በስር ፍርድ ቤት ከተረጋጠ ፍሬ ነገር አንፃር ሀሰተኛ ሰነድ መፍጠር እና መገልገል በመሆኑ ሰነዱም ለባል እና ሚስት ክርክር የቀረበ ሰነድ መሆኑ ከግምት ውስጥ ሲገባ በሀሰት የተዘጋጀውን ሰነድ መገልገሉን የሚያመለክት በመሆኑ ከቅጣት ውጤት አንፃር ተመሳሳይ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ስህተት የለውም ተብሎ ይፅናልን በማለት ተከራክሯል፡፡አመልካችም የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

ከላይ አጠር ባለ መልኩ የተገለጸዉ የግራ ቀኙን ክርክርና በክልሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠ ዉሳኔ ይዘት የሚመለከት ሲሆን በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል መሰረታዊ የሕግ ስህተት መፈጸም አለመፈጸሙን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነዉም ሕጉ-ወጥነቱና አስቀጪነቱ በሕግ የተደነገገዉን አንድን የወንጀል ድርጊት ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮችን በአንድነት በሟላ መልኩ መፈጸሙ በፍርድ ቤት የተረጋገጠበት ወንጀል ፈጻሚ በወንጀል ሕጉ አግባብነት ባለዉ ድንጋጌ መሰረት ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣት ይገባዋል፡፡በዚህ መልኩ ተከሳሹ ጥፋተኛ ሆኖ ሊቀጣ የሚችለዉ በተለይም በክሱ የተጠቀሰዉን የወንጀል ድርጊት ወይም አል ድርጊት አልፈጸምኩም በማለት ክዶ ከተከራከረ በወንጀል ሕጉ ልዩ ድንጋጌዎችና በሌላ ልዩ ሕግ በተለየ ሆኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ዐቃቤ ሕግ ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮችን በሚያሳይ አግባብ ተከሳሹ ወንጀሉን ስለመፈጸሙ በማስረጃ ሲያስረዳ ነዉ፡፡

በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 23 ማንኛዉም ሰዉ የሌዉን ሰዉ መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰዉ ተገቢ ያልሆነ ማናቸዉም መብት ወይም ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ መንግሥታዊ ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሰነዶችን አስመስሎ በማዘጋጀት ወይም በመፍጠር ፣ ወደ ሀሰት በመለወጥ ወይም በሐሰተኛ ሰነድ በመገልገል ተጠያቂ የሚሆነዉ በድንጋጌዉ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 3 ስር ተዘርዝረዉ የተጠቀሱትን ማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮች (አላባዎች) ተሟልተዉ ሲገኙ ነዉ፡፡እነዚህም አላባዎች፡-ሀ) አንድ መንግሥታዊ ወይም ሕዝባዊ ድርጅት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ጽሁፍ፣ መዝገብ ወይም ማንኛውንም ሰነድ በማስመሰል የተዘጋጀ ወይም የተፈጠረ እነደሆነ፤ ለ) በበመንግሥት ወይም በሕዝባዊ ድርጅት መዝገብ፣ በጽሁፍ ወይም በሠነድ የሰፈረን እውነተኛውን ጽሁፍ በመለወጥ ወይም በመደለዝ፣ በሀሰተኛ ፊርማ፣ በእጅ በተደረገ ምልክት ወይም በጣት ፊርማ፣ በማህተም ወይም የሌለውን ሥልጣን ወይም ችሎታ እንዳለው አስመስሎ በመፈረም ሀሰተኛ ሰነድ የተፈጠረ እንደሆነ፤ ወይም ሐ) አንድ ሠነድ በተለይም የፈራሚውን ስም ወይም ፊርማ ወይም የሰነዱን ይዘት፣ አሃዝ፣ ፍሬ ነገር ወይም ዝርዝር መግለጫ በሙሉ ወይም በከፊል በመለወጥ፣ በማሻሻል፣ በመቀነስ ወይም በመጨመር ወይም በማጥፋት ወደሀሰተኛነት ከተለወጠ ወይም ማናቸውንም ሀሰተኛ ፍሬ ነገር ያስገባ ወይም እንዲገባ ያደረገ እንደሆነ እና በዚህ አግባብ ወደ ሀሰት በተለወጠ ወይም በሀሰት በተዘጋጀ ሰነድ እያወቀ የተገለገለበት እንደሆነ የሚሉ ናቸዉ፡፡ ከዚህ ድንጋጌ አተገባበር ጋር በተያያዘ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 241756 ፣245579 እና በሌሎች መዛግብት ላይ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች የተከሰሰዉ በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 23(1/ሀ) ስር የተደነገገዉን በመተላለፍ የማይገባውን ጥቅም ለማግኘት እና ተበዳይ ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ በጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሸሪአ ችሎት በቁጥር 06135/2002 በቀን 22/08/2013ዓ.ም ከድንቅነሽ በቀለ ጋር በሀሰት ኒካ ያሰረ በማስመሰል እና ተበዳይ ድንቅነሽ በቀለን ወደ እስልምና እምነት በመቀየር ስሟን ሀያት በቀለ በሚል ሀሰተኛ የጋብቻ ምስክር ወረቀት በመፍጠር በገዋታ ወረዳ ፍርድ ቤት ከግል ተበዳይ ጋር ለነበራቸዉ ለባል እና ሚስት ክርክር አቅርቦ በመጠቀም በግል ተበዳይ ወ/ሮ ድንቅነሽ በቀለ ላይ ጉዳት ያአድርሷል በሚል ነዉ፡፡ አመልካች ሀሰተኛ ሰነድ አልፈጠርኩም በማለት የተከሰሰበትን ወንጀል ክዶ ተከራክሯል፡፡ ዐቃቤ ሕግ የግል ተበዳይን በምስክርነት አቅርቦ አሰምቶ አመልካች በክሱ የተጠቀሰዉን የጋብቻ ምስክር ወረቀት በሌላ ፍርድ ቤት ለነበራቸዉ ክርክር ማስረጃ አድርጎ መጠቀሙን አስረድቷል፡፡በዚህ አግባብ የተመሰከረዉን መሠረት በማድረግ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ክሱን እንዲከላከል አዝዞ አመልካች ባቀረበዉ ምስክር ከግል ተበዳይ ጋር በሸርአ ፍርድ ቤት ተገኝቶ ጋብቻ መፈጸሙን አስርድቷል፡፡ በተጨማሪም ሀሰተኛ ነዉ የተባለዉን ማስረጃ ሰጥቷል የተባለዉ ሸርአ ፍርድ ቤት ማስረጃ ተሰጠ የተባለዉን መዝገብ ማግኘት አለመቻሉን ገልጿል፡፡ በተገለጸዉ መሠረት ከተረጋገጠዉ ፍሬ ነገር አመልካች በክሱ የተጠቀሰዉን ሰነድ መገልገሉ ተረጋግጧል፡፡

ሆኖም ይህ አመልካች የተገለገለዉ ሰነድ ሀሰተኛ እንደሆነ እና ሀሰተኛ ሰነድ የፈጠረዉ አመልካች መሆኑ በተገቢዉ ማስረጃ መረጋገጡን የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ አያሳይም፡፡ሰነዱን ሰጠ የተባለዉ የሸርአ ፍርድ ቤት በማስረጃዉ ላይ በተጠቀሰዉ መዝገብ ቁጥር የሚታወቀዉ መዝገብ አልተገኘም የሚል መልስ መስጠቱ መዝገቡ ያልተገኘዉ ከመነሻዉም መዝገቡ የፍርድ ቤቱ ስላልሆነ ነዉ ወይስ መዝገቡ በፍርድ ቤቱ የነበረ ነገር ግን ፍርድ ቤቱ በፈለገበት ሰዓት መዝገቡ ባለመገኘቱ ምክንያት ነዉ? የሚሉ ጥያቄዎችን በማንሳት ተጨማሪ ማጣራት ተደርጎ እዉነታዉን መፈለግን አስፈላጊ የሚያደርግ ነዉ. እንጂ ተጠቃሹ ሰነድ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በአመልካች የተፈጠረ ሀሰተኛ ነዉ የሚል ድምዳሜ ላይ የሚያደርስ አይደለም፡፡ የዐቃቤ ሕግ ምስክር ከመሰከሩት በተጨማሪ ሰነዱ ሀሰተኛ ነዉ የሚል ድምዳሜ ላይ መድረስ የሚቻለዉ ሀሰተኛ በተባለዉ ሰነድ ላይ ያለዉ የግርጌ እና የራስጌ ማህተም እና በሰነዱ ላይ በዳኛ ወይም በሌላ ኃላፊ ተፈርሞ ከሆነ ፊርማ በፎረንሲክ ተመርምሮ ትክክለኛ ወይም በሀሰት የተዘጋጀ መሆኑን የሚያሳይ የሙያ ምስክርነት እንዲቀርብ ተገቢዉን ትዕዛዝ ሰጥቶ ማረጋገጥ ይገባል፡፡ እንዲሁም በሸርአ ፍርድ ቤቱ ምላሽ ላይ አልተገኘም ተብሎ የተገለጸዉ መዝገብ ያልተገኘዉ አስድሞም በተጠቀሰዉ ቁጥር የሚታወቅ መዝገብ ባለመኖሩ ነዉ ወይስ በምን ምክንያት ነዉ የሚለዉን ሸርዓ ፍርድ ቤቱ አጣርቶ ተጨማሪ ምላሽ እንዲልክ በማድረግ መዝገቡ ያልተገኘበትን ምክንያት ማወቅ ያስፈልጋል፡፡በዚህ መልኩ ተጨማሪ ትዕዛዝ ተሰጥቶ የሚቀርቡ ማስረጃዎችን እና አስቀድሞ ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ማስረጃዎች እና የምስክሮች ቃል ከእነ ሙሉ ይዘታቸዉ መርምሮና መዝኖ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ሰነድ ሀሰተኛ ሰነድ መሆን አለመሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡በዚህ አግባብ ሳያጣሩ ዉሳኔ መስጠት ማስረጃ አቀባበልና ምዘና መርሆዎችን እና በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23/2 የተደነገገዉን የወንጀል ሕግ መርህ አለመከተል እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 23 ስር የተደነገገዉን ግዙፋዊ ፍሬ ነገር በአግባቡ ሳያጣሩ መወሰን ይሆናል፡፡

ሲጠቃለል ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት አይቶ በአመልካች ላይ የጥፋተኝነት እና የቅጣት ዉሳኔ የሰጠዉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ሆነ ጉዳዩን በይግባኝ እና በሰበር አይቶ በትእዛዝ ያጸናዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከላይ በተመለከተዉ መሠረት ግዙፋዊ ፍሬ ነገር እንዲረጋገጥ እና አመልካች ሀሰተኛ ሰነድ መፍጠር አለመፍጠሩ ወይም ሀሰተኛ ሰነድ መገልገል አለመገልገሉን በተገቢዉ ማስረጃ እንዲረጋገጥ በማድረግ አግባብነት ያለዉን የሕግ ድንጋጌ መሠረት በማድረግ መወሰን ሲገባቸዉ በዚህ አግባብ ሳያጣሩ አመልካች ሀሰተኛ ሰነድ አዘጋጅቷል በሚል የጥፋተኝነት እና የቅጣት ዉሳኔ ማስተላለፋቸዉ ተረጋግጧል፡፡በዚህ መሠረት የተሰጠዉ ዉሳኔ የማስረጃ አቀራረብና ምዘና የሚመለከቱ መሠረታዊ መርሆዎችን የጣሰ ከመሆኑም በተጨማሪ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23/2 የተደነገገዉን የወንጀል ሕግ መርህ አተገባበር እና ከአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 23 አተገባበር ጋር በተያያዘ የተሰጠዉን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሚቃረን በመሆኑ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሸ) እና 10(1/ሐ) መሠረት ሊታረም የሚገባዉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## <u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. የካፋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ በመ/ቁጥር 21417 ላይ በቀን 09/06/2015ዓ/ም በአመልካች ላይ የሰጠዉ የጥፋተኝነትና የቅጣት ዉሳኔ፣የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 18015 ላይ በቀን 14/07/2015ዓ.ም የሠጠዉ ትዕዛዝ እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 14341 ላይ በቀን 18/08/2015ዓ.ም የሠጠዉ ትእዛዝ በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 መሰረት ተሽረዋል፡፡

<u>ማስታወሻ</u>፡- ይህ የሰበር ችሎት ዉሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

2. የካፋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ መዝገቡን በማንቀሳቀስ ከላይ በፍርድ ሀተታዉ ላይ በተገለጸዉ መሠረት ተጣርቶ እንዲቀርብ ተጨማሪ ትእዛዝ በመስጠት የሚቀርብለትን ማስረጃዎች መርምሮና መዝኖ የሚያረጋግጠዉን ፍሬ ነገር መሠረት በማድረግ ሕግን መሠረት ያደረገ ዉሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/2 መሠረት መልሰንለታል፡፡

## ትዕዛዝ

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ እንዲያዉቁት ለክልሉ ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡ ለግራ ቀኙም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. በዚህ የፍርድ ዉሳኔ መሠረት እንዲፈጽም የዉሳኔዉ ግልባጭ አመልካች ታስረዉ ለሚገኙበት ማረሚያ ቤት ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፍ/ደ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የመ.ቁ.247257

ጥቅምት 06/2017 ዓ.ም

ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች፡ ወ/ሮ ሐዋ ገልገሎ

ተጠሪ፡ አቶ ተማም ቱሉ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ጉዳዩ የባል እና ሚስት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የቀረበውም የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/422451 ላይ መጋቢት 11/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የአሁን አመልካችን የሰበር አቤቱታ ውድቅ ያደረገበትን ትዕዛዝ በመቃወም ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው የአሁን አመልካች ፍቺ እና የፍቺ ውጤትን አስመልክቶ በምዕራብ አርሲ ዞን ሀሳሳ ወረዳ ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ ባቀረቡት አቤቱታ ነው፡፡ በአቤቱታቸውም ከአሁን ተጠሪ ጋር በ2010 ዓ.ም ውስጥ በኦሮሞ ባህል መሰረት ጋብቻ ፈጽመው ሲኖሩ የነበሩ መሆኑን ጠቅሰው ጋብቻቸው በፍርድ ቤት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ውሳኔ ቀሪ ሆኖ የጋራ ንብረት ክፍፍል እንዲደርግ ጠይቀዋል፡፡ በዚሁ አቤቱታቸው ውስጥም የጋራ ንብረት ናቸው ያሏቸውን ጠቅሰው ያቀረቡ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ ለአሁኑ የሰበር ክርክር ምክንያት የሆነው በሀሳሳ ከተማ ቀበሌ 01 ክልል ውስጥ በ200 ካሬ ሜትር ይዞታ ላይ ያረፈ መኖሪያ ቤት ነው፡፡ ተጠሪ ለዚሁ አቤቱታ በሰጡት መልስ የተጠቀሰውን ቤት ከአመልካች ጋር ከመጋባታችን በፊት በ2011 ዓ.ም ውስጥ በግል ጥረቴ የሰራሁት እንጂ በጋብቻ ውስጥ የተፈራ አይደለም፤ ከአመልካች ጋርም በጋብቻ የቆየነው ከአንድ ዓመት ተኩል ላልበለጠ ጊዜ ብቻ በመሆኑ የጋብቻ ቆይታው የተጠቀሰውን ንብረት ለማፍራት የሚያስችል ባለመሆኑ አቤቱታው ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ጋብቻ በውሳኔ ቀሪ ካደረገ በኋላ በጋራ ንብረት ክርክሩ ላይ ማስረጃን ሰምቶ አሁን ክርክር የቀረበበትን ቤት ጨምሮ ሌሎች ንብረቶች የጋራ ንብረቶች ናቸው በሚል ተጠሪ ለአመልካች እንዲያካፍሉ ወስኗል፡፡ ተጠሪ ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት የይግባኝ አቤቱታ በትዕዛዝ ውድቅ በመደረጉ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ድጋሚ ይግባኝ አቅርበዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ በሰጠው ውሳኔ በጋብቻው ላይ የፍቺ ውሳኔ በሚሰጥበት ወቅት ጋብቻው የተመሰረተበትን ቀን አስመልክቶ በጭብጥነት ተይዞ አለመወሰኑ የሥነ ሥርዓት ግድፈት መሆኑን፤ በኦሮሚያ ቤተሰብ ህግ አንቀፅ 29(1) መሰረት ጋብቻ የሚፈፀመው ተጋቢዎች በአካል ተገኝተው ፍቃዳቸውን በማረጋገጥ ሲሆን በአካል ለመገኘት የማያስችል ከባድ ሁኔታ ሲያገጥም እና ለመጋባት ያላቸውን ፈቃደኝነት በማያጠራጥር ሁኔታ መግለፃቸው አግባብ ባለው የህግ አካል ሲረጋገጥ ጋብቻው በልዩ ሁኔታ በውክልና ሊፈፀም የሚችል መሆኑን፤ አመልካች ጋብቻ ተፈፀመ ባሉበት 2010 ዓ.ም ውስጥ በራሳቸው ሰውዲ አረቢያ፤ ተጠሪ ደግሞ ደቡብ አፍሪካ የነበሩ ስለመሆኑ በግራ ቀኙ የቀረቡት የሰው ምስክሮች ያረጋገጡ መሆኑን፤ ያም ሆኖ አመልካች ኒካ/ጋብቻው/ በውክልና ተፈፅሟል ከማለት ባለፈ በቤተሰብ ህጉ በተመለከተው አግባብ ግራ ቀኙ በልዩ ሁኔታ ተወክለው ጋብቻው ስለመፈፀሙ ያስረዱት ነገር እንደሌለ እና ጋብቻውን በውክልና ፈፅመዋል የተባሉት ግለሰቦችም በአግባቡ ስለመወከላቸው የተረጋገጠ ነገር እንደሌለ፤ ይልቁንም በተጠሪ በኩል ቀርበው የተሰሙት ምስክሮች ኒካው የታሰረው አመልካች ከሳውዲአረቢያ ከተመለሱ በኃላ በ2012 ዓ.ም ስለመሆኑ በተሻለ ሁኔታ ያስረዱ በመሆኑ እና ክርክር የተነሳበት የመኖሪያ ቤት ተጠሪ ከጋብቻ በፊት በ2011 ዓ.ም ያፈራው የግል ንብረቱ በመሆኑ አመልካች ሊካፈሉ አይገባም በማለት የስር ፍርድ ቤቶች ከዚህ አንጻር የሰጡትን ውሳኔ ሽሯል፡፡ አመልካች ይህንን በመቃወም ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም ችሎቱ በተሰጠው ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም በማለት በትዕዛዝ ውድቅ አድርጓል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ላይ ነው፡፡ አመልካች ግንቦት 14 ቀን 2015 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በክልሉ የባላይ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና ትዕዛዝ ላይ ተፈጽሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ መሰረታዊ ይዘቱም ግራ ቀኛችን የእስልምና ሀይማኖት በሚፈቅደው መሰረት ሰው ወክለን በ2010 ዓ.ም ጋብቻውን(ኒካ) ስለመፈፀማችን በወረዳው ፍ/ቤት ቀርበው በተሰሙ ምስክሮች ቃል ጭምር ተረጋግጦ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎት ጋብቻው የተፈጸመው ግራ ቀኙ አብረው መኖር ከጀመሩበት ከ2012 ዓ.ም አንስቶ ነው በሚል ክስ የቀረበበትን ንብረት እንዳልካፈል መወሰናቸው ከህግ አግባብ ውጭ ነው የሚል ነው፡፡

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በግራ ቀኙ መካከል ኒካ የታሰረው አመልካች በሳውድአረቢያ፤ ተጠሪ በደቡብ አፍሪካ ሆነው ስለመሆኑ ባልተካካዱበት ሁኔታ ጋብቻ የተፈፀመው በ2010 ዓ.ም ሳይሆን በ2012 ነው በሚል በክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች የተወሰነበት አግባብ ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀጽ 27(1)፤ የክልሉ ቤተሰብ ህግ አንቀጽ 29 እና ከዚሁ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ይኸው ችሎት ቀደም ሲል በመ/ቁ/213864 ላይ ከሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም አንጻር መርምሮ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ታዟል፡፡

በዚህም መሰረት ተጠሪ ግንቦት 15/2016 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ጋብቻው በ2010 ዓ.ም በውክልና ስለመደረጉ እንዳመነኩ ተደርጎ የተያዘው ጭብጥ ተገቢነት የሌለው ከመሆኑም በላይ በኦሮሚያ የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 83፣ 96 እና አንቀፅ 29(1) እንዲሁም በፌደራል የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 12 መሰረት ጋብቻ በልዩ ሁኔታ በውክልና በሚደረግበት ጊዜ ተጋቢዎች በማያጠራጥር ሁኔታ ፍላጎታቸውን ስለመግለፃቸው በሀገሪቱ ፍትህ ሚኒስቴር የተረጋገጠ ውክልና ሊቀርብ ይገባል፡፡ ጉዳዩ ከህገመንግስቱ አንቀፅ 27 ከተረጋገጠው የፈለጉትን ሀይማኖት ከመከተል ነፃነት ጋር የሚያገናኘው ጉዳይ የሌለ ሲሆን በሰ/መ/ቁ/213864 የተሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉምም ጋብቻ በልዩ ሁኔታ በውክልና መፈፀም እና ማፍረስ እንደሚቻል ከሚገልፅ በስተቀር አሁን ከተያዘው ጉዳይ ጋር ግንኙነት የለውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በስር ፍ/ቤት ጋብቻው የተፈፀመው በ2012 ዓ.ም ስለመሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ እና ውሳኔው በተገቢው ማስረጃ ተጣርቶ የተሰጠ በመሆኑ ሰበር ሰሚ ችሎቱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም በማለት የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤረቱታቸውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ በመስጠት ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር ከተጠናቀቀ በኋላ ይኸው ችሎት ቀደም ሲል በመ/ቁ/213864 ላይ የሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም እንዲሁም በእንደራሴ አማካኝነት የሚፈፀም ኃይማኖታዊ ጋብቻን አስምልክቶ በቤተሰብ ህጉ የተመለከተው ዝርዝር የአፈፃፀም ስርዓት ህገ መንግስታዊነቱ ሰባት ዳኞች ለሚሰየሙበት ችሎት ቀርቦ ትርጉም እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡ በዚሁ መሰረት ሰባት ዳኞች የተሰየሙበት ሰበር ሰሚ

ችሎት በዚሁ መዝገብ ላይ ነሓሴ 21/2016 ዓ.ም በዋለው ችሎት ቀድሞ የተሰጠው የህግ ትርጉም ሊለወጥ አይገባም፤ ጉዳዩም የህገ መንግስት ትርጉም የሚያስነሳ አይደለም በማለት በዋናው የክርክር ነጥብ ላይ እንዲወሰን መዝገቡን መልሷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና መሰረታዊ የክርክሩ ይዘት ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ አመጣጥ መገንዘብ የተቻለው ግራ ቀኙን እስከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ እያከራከረ ያለው በመካከላቸው በህግ ፊት የፀና ጋብቻ የተፈፀመበትን ቀን አስመልክቶ እንደሆነ ነው፡፡ ከዚሁ ጉዳይ ጋር በተያያዘ አመልካች የፍቺ ጥያቄ ባቀረቡበት የክስ አቤቱታቸው ጋብቻው የተፈፀመው በ2010 ዓ.ም ውስጥ በኦሮሞ ባህል መሰረት መሆኑን፤ በኋላ ባለው ክርክር ደግሞ የጋብቻ አፈፃፀም ስርዓቱ በእስልምና ሃይማኖ ሆኖ ግራ ቀኙ ውጭ ሀገር ሆነው በቤተሰብ ተወካዮቻቸው በኩል በተሰጠ ፈቃደኝነት በ2010 ዓ.ም ኒካ ታስሮ የነበረ መሆኑን ጠቅሰው የሚከራከሩ እንደሆነ፤ ተጠሪ በበኩላቸው ኒካ ታሰረ በተባለበት በ2010 ዓ.ም ከሀገር ውጭ የነበሩ ሲሆን አመልካች በጠቀሱት አኳኋን ጋብቻ እንዲፈፀም የሰጡት ፈቃደኝነት አለመኖሩን፤ በመካከላቸው ኒካ የታሰረውም ሆነ የተጋቡት በ2012 ዓ.ም ሁለቱም ከነበሩበት ውጭ ሀገር ከተመለሱ በኋላ መሆኑን በመግለፅ የጋብቻው ጊዜ ይኸው ቀን እንደሆነ ጠቅሰው የሚከራከሩ መሆኑን ነው፡፡

እንግደህ ጋብቻ ተቋም በመሆኑ የሚቋቋመው ለአፈፃፀሙ በህግ ተለይቶ በተመለከተው አግባብ ነው፡፡ አፈፃፀሙን አስመልክቶም ቀዳሚ መሰረቱ የተጋቢዎቹ ሙሉ ፈቃድ ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀፅ 34/2/ ስር ተመልክቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ህገ መንግስቱ በህግ በተለይ በሚዘረዘረው መሰረት በሃይማኖት፤ በባህል የህግ ስርዓቶች ላይ ተመስርተው ለሚፈፀሙ ጋብቻዎች እውቅና የሚሰጥ ህግ ሊወጣ እንደሚችል በዚሁ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 4 ስር ተመልክቷል፡፡ ይህንኑ የህገ መንግስት ድንጋጌን መሰረት አድርገው በታወጁት የፌዴራሉ የቤተሰብ ህግ እና የክልል የቤተሰብ ህግጋት የጋብቻ አፈፃፀም ስርዓት ዓይነቶች፤ ለህጋዊነታቸው መሟላት የሚገባቸው መሰረታዊ መስፈርቶች እና ዝርዝር የአፈፃፀም ሁኔታዎች ተደግገዋል፡፡

በዚሁ መሰረት ጋብቻ በሶስት ዓይነት የጋብቻ ማስፈፀሚያ ሥርዓቶች የሚፈፀም መሆኑን፤ እነዚህም በክብር መዝገብ ሹም ፊት የሚፈፀም ጋብቻ፤ በሐይማኖት ሥርዓት መሰረት የሚፈፀም ጋብቻ እና በባህል ሥርዓት መሰረት የሚፈፀም ጋብቻ ስለመሆኑ በተሻሻለው የፌዴራል መንግስቱ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 1 ስር ተመልክቷል፡፡ በእነዚህ የጋብቻ ማስፈፀሚያ ሥርዓቶች

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

መካከል በአፈፃፀሙ ረገድ ልዩነት ያለ ቢሆንም ጋብቻው በየትኛውም ሥርዓት ቢፈፀም ሊታለፉ የማይችሉ እና በሶስቱም የማስፈፀሚያ ስርዓቶች ላይ ተፈፃሚነት ያላቸው መሰረታዊ ቅድመ ሁኔታዎች ወይም የጋራ መለኪያዎች በቤተሰብ ህጉ ክፍል ሁለት ስር ከአንቀጽ 6 እስከ 16 ተዘርዝረዋል፡፡ እነዚህ አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎች አለመሟላታቸው የታወቁት በጋብቻ ዝግጅት ወቅት ከሆነ ጋብቻው እንዳይፈፀም በህግ መብቱ በተሰጣቸው አካላት መቃወሚያ አቅራቢነት ከመፈፀም ሊታገድ የሚቻል መሆኑን፤ የሁኔታዎቹ አለመሟላት ጋብቻው ከተፈፀመ በኋላ የታወቀ ከሆነ ደግሞ በጉድለቱ ምክንያት የተመሰረተው ጋብቻ በፍርድ ቤት ውሳኔ ቀሪ እንዲሆን አቤቱታ ማቅረብ የሚቻል ስለመሆኑ ከአንቀጽ 31- 39 ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

በቤተሰብ ህጉ ለሶስቱም የጋብቻ ማስፈጸሚያ ሥርዓቶች ህጋዊነት መሰረታዊ መመዘኛ ተብለው ከተመለከቱት ውስጥ ቀዳሚው የተጋቢዎቹ ፈቃድ ነው፡፡ እንግዲህ ጋብቻ በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ለአካለ መጠን በደረሱ አንድ ወንድ እና አንዲት ሴት መካከል ለዘለቄታው በጋብቻ አብሮ በመኖር ሀሳብ የሚደረግ የቃልኪዳን ስምምነት ነው፡፡ የዚህ ዓይነት ስምምነት ደግሞ የህብረተሰብ የተፈጥሮ መሰረት የሆነው ቤተስብ የሚፈራበት ህጋዊ ተቋም በመሆኑ በተጋቢዎቹ ነጻና ሙሉ ፈቃድ ላይ የተመሰረተ ሊሆን ይገባል፡፡ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀፅ 34/2/ ስር ጋብቻ በተጋቢዎች ነፃና ሙሉ ፈቃድ ላይ ብቻ ይመሰረታል በሚል የተደነገገውም ከዚሁ በመነሳት ነው፡፡ በቤተሰብ ህጉ አንቀጽ 6 ስር ከተጋቢዎች ነፃ ፈቃድ አኳያ የተቀመጠው የህጋዊነት መለኪያም የዚሁ ህገ መንግስት ድንጋጌ ነጸብራቅ ነው ተብሎ ሊወሰድ የሚችል ነው፡፡

የፈቃድ አሰጣጡም ሊፈፀም ስለሚገባበት አኳኋን በቤተሰብ ህጉ አንቀጽ 12 ስር ተመልክቷል፡፡ በዚሁ መሰረት ዋና መርሆው ሁለቱም ተጋቢዎች ጋብቻው በሚፈፀምበት ጊዜ በግንባር ተገኝተው ፈቃዳቸውን መስጠት ያለባቸው ስለመሆኑ በድንጋጌው ንዑስ አንቀጽ /1/ ስር ተመልክቷል፡፡ በዚህ መልኩ በግንባር ተገኝቶ ፈቃደኝነቱን ከመስጠት ያገደው ከባድ ምክንያት ያለው ተጋቢ በእንደራሴው አማካኝነት ጋብቻውን ሊፈጽም እንደሚችል፤ በእንደራሴ አማካኝነት ጋብቻው ሊፈፀም የሚችለውም ተጋቢው ፈቃዱን በማያሻማ ሁኔታ የገለፀ ስለመሆኑ የፍትሕ ሚኒስትሩ ሲያረጋግጥ እንደሆነ በንዑስ አንቀጽ 2 ስር ተመልክቷል፡፡ እነዚህ የጋብቻ ማስፈፀሚያ ስርዓቶችም ሆኑ ለህጋዊነታቸው መሰረት ናቸው ተብለው በማዕከላዊ መንግስቱ የቤተሰብ ህግ ውስጥ ከተመለከቱት መመዘኛዎች ውስጥ በእንደራሴ አማካኝነት ሊፈፀም የሚችለው ጋብቻ በክልሉ ፍትህ ቢሮ ኃላፊ እንዲረጋገጠ ከመደረጉ ውጭ የተቀሩቱ ቃል በቃል ሊባል በሚችል አኳኋን በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቤተሰብ ህግ ውስጥ የተካተቱ ስለመሆኑ ከክልሉ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 69/1995(በአዋጅ ቁጥር 83/1996 እንደተሻሻለው) አንቀጽ 19/1/ እንዲሁም ከአንቀጽ 25-33 ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አሁን በቀረበው ጉዳይ አመልካች በጽሁፍ ባቀረቡት አቤቱታቸው ጋብቻው በኦሮሞ ባህል ስርዓት መሰረት የተፈፀመ መሆኑን አመልክተው የነበረ ሲሆን በክርክር ሂደት ግለጽ ባልሆነ ምክንያት የጋብቻ አፈፃፀም ስርዓቱ ሃይማኖታዊ እንደሆነ ተጠቅሷል፡፡ ተጠሪም ቢሆኑ ጋብቻው የተፈፀመበትን ትክክለኛ ቀን አስመልክቶ ክርክር ከማቅረባቸው ውጭ አፈፃፀሙ የእስልምና ሐይማኖትን መሰረት ባደረገ መልኩ በመሆኑ ጉዳይ ላይ ክርክር የላቸውም፡፡ በመሆኑ በግራ ቀኙ መካከል የተፈፀመው ጋብቻ የእስልምና ሐይማኖት ስርዓትን በተከተለ መልኩ ነው የሚለውን ይኸው ችሎትም ተቀብሏል፡፡ የተፈፀመበትን ቀን አስመልክቶ አመልካች 2010 ነው ሲሉ ተጠሪ በበኩላቸው በ2012 ዓ.ም እንደሆነ ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡ በአመልካች መከራከሪያ መሰረት ኒካው ታስሯል በተባለበት 2010 ግራ ቀኙ በሀገር ውስጥ ያልነበሩ ስለመሆኑ የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የአመልካች ዋነኛ መከራከሪያ ባለንበት ሀገር ሆነን ለጋብቻው መፈፀም በሰጠነው ፈቃደኝነት መሰረት ጋብቻው በቤተሰቦቻችን አማካኝነት ተፈጽሟል፣ የዚህ ዓይነት የአፈፃፀም ስርዓትም በእስልምና ኃይማኖ የተፈቀደ በመሆኑ በጋብቻው ጊዜ በአካል መገኘት ግዴታ አይደለም የሚል ነው፡፡

በእርግጥ በሃይማኖት ወይም በባህል የህግ ስርዓቶች ላይ ተመስርተው ለሚፈፀሙ ጋብቻዎች እውቅና የሚሰጥ ልዩ ህግ ሊወጣ እንደሚችል በህገ መንግስቱ ተመላክቷል፡፡ ይህንኑ የህገ መንግስቱን ድንጋጌ መሰረት በማድረግም ጋብቻን እና አፈፃፀሙን የሚገዙ ዝርዝር የህግ ድንጋጌዎች የያዘ የክልሉ የቤተሰብ ህግ ወጥተዋል፡፡ በእነዚህ ልዩ ዝርዝር ድንጋጌዎችም ለጋብቻ አፈፃፀም የተጋቢዎቹ ሙሉ ፈቃደኝነት መሰረታዊ መመዘኛ መሆኑን እና ፈቃደኝነቱ የሚሰጠውም በጋብቻው ጊዜ በግንባር በመገኘት መሆኑን፣ ጋብቻው በእንደራሴ በኩል መፈፀም የሚቻለው አንደኛው ተጋቢ በጋብቻው ጊዜ በግንባር ለመገኘት ከባድ ምክንያት የገጠመው ሆኖ ለጋብቻው ያለውን ፈቃደኝነት በማያሻማ አኳኋን ስለመግለፁ በክልሉ ፍትሕ ቢሮ ኃላፊ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡

ከላይ እንደተመለከተው የጋብቻ አፈፃፀምን አስመልክቶ በመሰረታዊ የህጋዊነት መመዘኛነት የተመለከቱን የአፈፃፀም ስርዓቶች ለእያንዳንዱ የጋብቻ ማስፈፀሚያ ስርዓት የተተወ ሳይሆን በሶስቱም የጋብቻ ማስፈፀሚያ ስርዓቶች ላይ በእኩል ተፈፃሚነት ያላቸው ናቸው፡፡ እናም ጋብቻው በኃይማኖታዊ ስርዓት መፈፀሙ ለጋብቻ አፈፃፀም ህጋዊነት የተቀመውን መሰረታዊ መመዘኛ ቀሪ የሚያደርገው አይደለም፡፡ ከዚሁ ጉዳይ ጋር በተያያዘም ይኸው ችሎት ቀደም ሲል በመ/ቁ/213864 ላይ ሚያዝያ 28/2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሃይማኖታዊ ስርዓት መሰረት የሚፈፀም ጋብቻ በቤተሰብ ህጉ ለጋብቻ አፈፃፀም መሰረታዊ መመዘኛ ተብለው የተመለከቱትን ዝርዝር መመዘኛዎችን ማሟላት የሚገባው ስለመሆኑ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ ከዚህ ችሎት የሚሰጥ የህግ ትርጉም ደግሞ ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በማናቸው ደረጃ ላይ በሚገኙ የፌደራልም ሆነ የክልል ፍርድ ቤቶች

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ላይ የአስገዳጅነት ኃይል ያለው ስለመሆኑ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 ተደንግጓል፡፡

ከዚህ አንፃር የአመልካች መከራከሪያ በ2010 ዓ.ም ተደረገ የተባለው የኒካ ሥነ ሥርዓት/ጋብቻ/ በእንደራሴ አማካኝነት የተፈፀመ ሆኖ የእንደራሴ ጋብቻ አፈፃፀሙ በክልሉ የቤተሰብ ህግ መሰረት የተከናወነ እንዳልሆነ ማስረጃን በመመርመር እና በመመዘን ረገድ የመጨረሻ የዳኝነት ስልጣን ባለው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተረጋግጧል፡፡ የኒካ ሥነ ሥርዓቱ ከተጋቢዎቹ ነፃ ፈቃደኝነት አሰጣጥ ጋር ተያይዞ በልዩ ህጉ የተመለከተውን መመዘኛ ያላሟላ ከሆነ ደግሞ ኒካው/ጋብቻው/ ተፈጽሟል ለማለት አይቻልም፡፡ በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በዚሁ ጉድለት ምክንያት በግራ ቀኙ መካከል በ2010 ዓ.ም ጋብቻ አልተፈፀመም በሚል መወሰኑ እና ሰበር ችሎቱም ይህንኑ መቀበሉ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት፣ የክልሉን የቤተሰብ ህግ እና ከዚህ ችሎት በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ የተሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የተከተለ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍበት መሰረታዊ የህግ ስህተት ባለመኖሩ የአመልካች መከራከሪያ ውድቅ ተደርጎ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚው ችሎት በመ/ቁ/422451 ላይ መጋቢት 11/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ ቁጥር 348(1) እና የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1/ሀ// መሰረት ፀንቷል፡፡

## ትዕዛዝ

1. የዚህን ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ ካለ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሶስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፍ/

## የህሳብ ልዩነት

እኛ በሶስተኛ እና አምስተኛ ተራ ቁጥር ስማችን የተጠቀሰው የችሎቱ ዳኞች አብላጫው ድምፅ ቀደም ሲል በመ/ቁ/213864 ላይ የተሰጠው የህግ ትርጉም ህገ መንግስቱን እና እርሱን መሰረት አድርጎ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የወጣውን ልዩ ህግ መሰረታዊ ዓላማ እና መንፈስ የተከተለ በመሆኑ የትርጉም ለውጥ አያስፈልገውም በሚል በደረሰበት መደምደሚያ ያልተስማማን በመሆኑ ያለንን የልዩነት ሀሳብ እንደሚከተለው አሥፍረናል ፡፡

በግራ ቀኙ መሃል ያለው ክርክር የፍቺ ውጤትን አስመልክቶ ጋብቻው በህጉ አግባብ የተመሰረተው መቼ ነው የሚለውን መሰረታዊ ነጥብ መሰረት አድርጎ የተነሳን የንብረት ክፍፍል የሚመለከት ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትና ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ አመልካች ጋብቻችን ከ2010 ዓም ጀምሮ ተመስርቷል በማለት የሚያቀርቡትን ክርክር ውድቅ በማድረግ ግራ ቀኙ እንደ ባልና ሚስት ሆነው አብረው መኖር የጀመሩት ከ20/06/2012 ዓም ጀምሮ ነው በማለት የደመደሙት በ2010 ዓም አመልካች ሳውዲ አረቢያ ተጠሪ ደግሞ ደቡብ አፍሪካ በመሆን ግራ ቀኙ ባልተገኙበት በቤተሰቦቻቸው የታሰረው ኒካ በክልሉ የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 29(2) መሰረት ግራ ቀኙ በአካል ለመገኘት የማያስችል ሁኔታ ያላቸው መሆኑ ተረጋግጦ በማያጠራጥር ሁኔታ ፍቃዳቸውን በመግለፅ ጋብቻውን መፈፀማቸው በተገቢው አካል አለመረጋጡን በመጥቀስ ነው፡፡

በመሰረቱ አንዳንድ የሀይማኖቱ ምሁራን እና ፀሀፍት ከተጋቢዋ በተጨማሪ ሞጊዝትና አስተዳዳሪዋ (Wali) ጋብቻውን አስመልክቶ ፈቃዱን ሊሰጥ የሚገባ መሆኑን የሚያመለክቱ ቢሆንም ተጋቢዋን በተመለከተ ግን የተጋቢዋ ግልፅና የማያሻማ ፈቃድ (Explicit Consent) ለጋብቻው መመስረት መሰረታዊ መስፈርት መሆኑን ተመሳሳይ በሆነ ሁኔታ አስፍረዋል፡፡ለማሳያነትም ኢስላምን ወደ ቁርአንና ሱናህ ለመመለስ በጥብቅ መስራቱ የተመሰከረለት የ13ኛው ክፍለ ዘመን ታዋቂ ሀይማኖታዊ መምህር ኢብኑ ታያሚያህ “As for marrying off a woman who is averse to the marriage, it is contrary to both the principles of Shari'ah and the sound intellect. Allah, Exalted is He, does not allow her guardian to compel her to sell or lease contracts except with her permission; neither does He allow the guardian to compel her to food, drink or dress; so how can He [Allah] compel her to have a relationship with someone she hates.” በሚል ማስፈሩም እንደ ሀገራችን የቤተሰብ ህግ ሁሉ በኢስላምም የተጋቢዋ/የተጋቢው ፈቃድ መሰረታዊ መስፈርት መሆኑን፣ይህንን መሰረታዊ መስፈርት ያላሟላ ትዳር ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ያሳያል፡፡ይህም በኢፌዲሪ ህገ መንግሰት አንቀፅ 34(2) ስር ጋብቻ በተጋቢዎች ነፃና ሙሉ ፈቃድ ላይ ብቻ የሚመሰረት መሆኑ መመልከቱና በቤተሰብ ህጉ አንቀፅ 6 ስር ከተጋቢዎች ነፃ ፈቃድ አንጻር የህጋዊነት መለኪያ መቀመጡ በመሰረታዊነት በሸሪዓ ህጉ ከተመለከተው አንፃር ልዩነት የሌለው መሆኑን ፣ከነፃና ሙሉ ፈቃድ ጋር በተያያዘ ተመሳሳይ መስፈርት ያስቀመጡ መሆኑን ያሳያል፡፡ለልዩነት ሀሳባችን መነሻችንም ሆነ መደምደሚያችን ይህ ነፃና ሙሉ ፈቃድ የሚገለፅበትን አግባብ መሰረት ያደረገ ነው፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በመሰረቱ በመርህ ደረጃ ለጋብቻ አፈፃፀም የተጋቢዎቹ ሙሉ ፈቃደኝነት መሰረታዊ መመዘኛ መሆኑን፤ፈቃደኝነቱ የሚሰጠውም በጋብቻው ጊዜ በግንባር በመገኘት መሆኑን የክልሉ የቤተሰብ ህግ የሚደነግግ ሲሆን ፤ለዚህ መርህ ቀሪ ሁኔታን ያበጀው የቤተሰብ ህጉ ጋብቻን በእንደራሴ በኩል መፈፀም የሚቻለው አንደኛው ተጋቢ በጋብቻው ጊዜ በግንባር ለመገኘት ከባድ ምክንያት የገጠመው ሆኖ ለጋብቻው ያለውን ፈቃደኝነት በማያሻማ አኳኋን ስለመገለፁ በክልሉ ፍትህ ቢሮ ሀላፊ ሲረጋገጥ <u>ብቻ</u> እንደሆነ መደንገጉ በሌላ አነጋገር የክልሉ ቤተሰብ ህግ በእስልምና ሃይማይኖት የሸሪዓ ህግ መሰረት አንዲት ሴት ለመጋባት በወላጅ አባቷ ፣ አባት ከሌላት በታላቅ በወንድሟ፤ወንድሟ ከሌለም በአጎቷ  በኩል ሙሉ እና ነፃ ፈቃዱን ሰጥታ ነገር ግን በስፍራው በአካል ሳትገኝ በውክልና ኒካ የሚታሰርበትን አግባብ  በተጨማሪ ቀሪ ሁኔታነት አለማካተቱ ማንም ሰው የመረጠውን ሀይማኖት የመከተልና የመተግበር መብት ተጠብቆለታል በሚል በክልሉ ህገመንግስት አንቀፅ 27(1) የተመለከተውን እንዲሁም በህግ በተለይ በሚዘረዘረው መሰረት በሀይማኖት ስርዓቶች ላይ ተመስርተው ለሚፈፀሙ ጋብቻዎች እውቅና የሚሰጥ ህግ ሊወጣ እንደሚችል የሚደነግገውን የህገ መንግስቱን አንቀፅ 34(4) ባላማከለ መልኩ ህጉ መውጣቱን ያሳያል፡፡

በሸሪዓ ህጉ መሰረት እየአንዳንዱ ጋብቻ ሲፈፀም ሴትና ወንድ ተቀላቅለው ሊቀመጡ የማይችሉ በመሆኑ ሴቷ በጋብቻ ስርዓቱ ወቅት በግንባር የምትገኝበት አግባብ የሌለ መሆኑ፤ ከዚህ ይልቅ በሀይማኖቱ ስርዓት መሰረት ነፃና ሙሉ ፈቃዷ በተወካይዋ አማካኝነት የሚረጋገጥበት ነባራዊ ሁኔታ ተግባራዊ የሚደረግ መሆኑ የተለመደ ሆኖ እያለ፤እንዲሁም ተጋቢዎቹ በተለያየ ሀገር ከሆኑም በሀይማኖቱ ስርዓት መሰረት ተጋቢዎቹ ተገቢውን ተወካያቸውን መርጠው  በተወካያቸው አማካኝነት ነፃና ሙሉ ፈቃዳቸውን መስጠታቸው እየተረጋገጠ ጋብቻ የሚፈፀም ሆኖ እያለ በዚህ አግባብ በሀይማኖቱ ስርዓት ለሚፈፀመው ጋብቻ እውቅና የሚነፍገውን የቤተሰብ ህግ፤ የሕገ መንግስቱን ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ ጋብቻን እና አፈፃፀሙን የሚገዛ ዝርዝር የሕግ ድንጋጌዎች የያዘ የቤተሰብ ህግ መሆኑን በማመልከት፤ይህንኑ የቤተሰብ ህግ መሰረት በማድረግ አስገዳጅ የህግ ትርጉም መስጠት ነባራዊ ሁኔታውን ያገናዘበ ነው ብለን አናምንም፡፡

ይህ ከሆነ ደግሞ በየደረጃው ያሉት የክልሉ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ወደ ተገቢው የህገ መንግስት ተርጓሚ አካል በመምራት ተገቢው የህግ ትርጉም እንዲሰጥ ሊያደርጉ ሲገባ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ.213864 ተመሳሳይ ይዘት ያለውን የደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መንግስት የቤተሰብ ህግ መነሻ በማድረግ የሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሰረት በማድረግ  መወሰናቸው አግባብ ነው ብለን ስለማናምን፤ አብላጫው ድምፅ ለውሳኔው መሰረት ያደረገው በሰ/መ/ቁ.213864 ተመሳሳይ ይዘት ያለውን የደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መንግስት የቤተሰብ ህግ መነሻ በማድረግ የተሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉምም የኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 27(1) እና 34(4) ን መሰረት ያደረገ ነው ሊባል ስለማይችል፤ የጋብቻ

<u>ማስታወሻ</u>፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አፈፃፀምን አስመልክቶ በቤተሰብ ህጉ የተመለከተው ዝርዝር ስርዓት በህግ መንግስቱ ለሐይማኖታዊ ጋብቻ አፈፃፀም ስርዓቶች የተሰጠውን እውቅና የሚያጣብብ፤በሀይማኖት ስርዓቶች ላይ ተመስርተው ለሚፈፀሙ ጋብቻዎች እውቅና የሚሰጥ ህግ ለማውጣት የተገባውን ግዴታ የማያከብር እና ከዚህ አንፃርም የቤተሰብ ህጉ ከህገ መንግስቱ ጋር የሚጣረስ በመሆኑ ጉዳዩ ሰባት ዳኞች በሚሰየሙበት ችሎት ቀርቦ ታይቶ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የፌዴሬሽን ምክር ቤት ቀርቦ ህገ መንግስታዊ ትርጉም እንዲሰጥበት ሊመራ  ይገባል በማለት ከስራ ባልደረባዎቻችን በሀሳብ ተለይተናል፡፡

የማይነበብ የሁለት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፍ/ደ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የሰበር መ/ቁ 247259

ጥቅምት 04 ቀን 2017 ዓ/ም

ዳኞች - ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻዉ አዳነ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሰናይት አድነዉ

ሀፊዝ አባጀማል

አመልካች ፦ ወ/ሮ ወይኒ ወ/ሀይማኖት ተክኤ

ተጠሪ ፦ 1. ወ/ሮ ፀሐይ ተሾመ ወልደ ሐዋርያት

2. አቶ የኔነህ ወርቁ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከለታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 179184 ነሐሴ 10 ቀን 2014 ዓ/ም ያሳለፈዉን ብይን እና ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 297146 የካቲት 13 ቀን 2015 ዓ/ም የሰጠዉን ዉሳኔ በመቃወም ነው፡፡ ክርክሩ የጀመረው የአሁን አመልካች በተጠሪዎች ላይ በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ነበር፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው አመልካች በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ምክንያት ከኢትዮጵያ ወደ ኤርትራ የሄድኩ ሲሆን በዚህ ጊዜ በቀድሞዉ ወረዳ 20 ቀበሌ 51 በአሁኑ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወራዳ 05 የቤት ቁጥር 918 ተመዝግቦ የሚገኘዉን መኖርያ ቤት እንዲያስተዳደሩልኝ በዉክልና ለ1ኛ ተጠሪ ሰጥቸ የሄድኩ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ ከእኔ እዉቅና ዉጭ ለባለቤታቸዉ ለ2ኛ ተጠሪ በሽያጭ ያስተላለፉ መሆኑን ህዳር 22 ቀን 2014 ዓ/ም ወደ ኢትዮጵያ በተመለስኩ ግዜ ያወቅኩ በመሆኑ የሽያጭ ዉሉ ፈራሽ ነዉ ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪዎች ለክሱ ባቀረቡት መቃወሚያ ክሱ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 222(1)(ሐ)(ረ) መሰረት የቀረበ ባለመሆኑ ስነስርዓታዊ አይደለም፤ ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉ ቤት እና ቦታ ይዞታዉ ተለዉጦ ግምቱ ከፍያለ ንብረት ያለበት በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለዉም፤ አመልካች በክሱ ተሸጠ ያሉት ቤት አሁን ላይ ስለመኖሩ ማስረጃ ያላቀረቡ በመሆኑ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል የክስ ምክንያት የላቸዉም፤ አመልካች ክሱን ለማቅረብ መብት እና ጥቅም የላቸዉም፤ እንዲሁም ክሱ በይርጋ የታገደ በመሆኑ ልንጠየቅ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የስር ፍርድ ቤት በቀረበዉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ የግራቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኃላ ክሱ ስነስርአታዊ አይደለም፤ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለዉም፤ እንዲሁም አመልካች ክስ ለማቅረብ የሚያስችል የክስ ምክንያት የላቸዉም የሚለዉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ተቀባይነት የለዉም ብሏል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች ክስ ለማቅረብ መብት እና ጥቅም የላቸዉም በሚል የቀረበዉን መቃወሚያ በተመለከተ አመልካች በ1990 ዓ/ም በፊት በአዲስ አበባ ከተማ ሲኖሩ በወቅቱ በኢትዮጵያ እና ኤርትራ መካከል በነበረዉ አለመግባባት ምክንያት አመልካች ከሀገር ለቀዉ ሲወጡ ሀምሌ 01 ቀን 1990 ዓ/ም ለ1ኛ ተጠሪ ቤቱን እንዲያስተዳድሩ፣ እንዲሸጡ እና እንዲለዉጡ በሚል በሰጡት ዉክልና እና በወቅቱ በነበረዉ የመንግስት መመርያ መሰረት ቤቱ የተሸጠ እና በቦታዉ የነበረዉ ቤት ፈርሶ ፎቅ ህንፃ የተሰራበት ሲሆን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ግንቦት 07 ቀን 2001 ዓ/ም ባካሄደዉ 85ኛ መደበኛ ስብሰባ ባወጣዉ መመርያ አንቀፅ 4 መሰረት ንብረቱ የተሸጠባቸዉ ኤርትራዊያን ንብረታቸዉን ለማግኘት የሚችሉት ንብረቱን በማስመለስ ሳይሆን በዝግ አካዉንት የተቀመጠላቸዉን ገንዘብ በመዉሰድ ብቻ መሆኑን የሚያስረዳ በመሆኑ አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ በሰጡት ዉክልና መሰረት ቤቱ የተሸጠ በመሆኑ በዝግ አካዉንት የተቀመጠ ገንዘብ ካለ ገንዘቡን ከሚጠይቁ በስተቀር የሽያጭ ዉሉ እንዲፈርስ ዳኝነት ለመጠየቅ የክስ ምክንያት የላቸዉም፡፡ እንዲሁም ይርጋን በተመለከተ የሽያጭ ዉሉ የተደረገዉ ግንቦት 23

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ቀን 1992 ዓ/ም በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ 2187(1) መሰረት በዉክልና መነሻነት ሽያጭ ሲፈፀም ዉሉ ሊፈርስ የሚችለዉ ወካዩ (ሸዋሚዉ) ስለ ሽያጩ ካወቀበት ቀን ጀምሮ በሁለት አመት ዉስጥ የሽያጭ ዉሉ እንዲፈርስ ካልጠየቀ የዉል ይፍረስልኝ ጥያቄ በይርጋ እንደሚታገድ የተደነገገ በመሆኑ እና አመልካች ሽያጩ እንደተፈፀመ ያወቀኩት ህዳር 14 ቀን 2014ዓ/ም ነዉ ይበሉ እንጂ ተጠሪ ምስክሮች ቤቱ ሲሸጥ ተጠሪ ለአመልካች እንዳሳወቋቸዉ እና ስለ ሽያጩ እንደሚያዉቁ ያስረዱ በመሆኑ የአመልካች ክስ በሁለት አመት ይርጋ ታግዷል በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝተዉ ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱ በቀረበዉ ይግባኝ አቤቱታ ላይ ግራቀኝን አከራክሮ የስር ፍርድ ቤት ያሳለፈውን ብይን በማፅናት ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው፡፡ አመልካች ግንቦት 14/2015 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ተፈፀመ የሚሉትን መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱ ባጭሩ የስር ፍርድ ቤት ለብይኑ መሰረት ያደረገው ግንቦት 07 ቀን 2001 ዓ/ም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ያወጣዉ መመርያ ሲሆን ይህ መመርያ የኤርትራዊን ንብረት ተሸጦ በባንክ የተቀመጠ የሽያጭ ገንዘብ ካለ ገንዘቡ ለባለንብረቶቹ እንዲመለስ ንብረቱ ካልተሸጠ ደግሞ ንብረቱ ለባለንብረቶች እንዲመለስ የሚፈቅድ መመርያ እንጂ ግለሰቦች በዉክልና የተቀበሉትን አደራ ጥሰዉ የወካዮቻቸዉን ንብረት በመሸጥ ለግል ጥቅማቸዉ እንዲያዉሉ መብት የሚሰጥ መመርያ አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪዎች በህግ ፊት ተቀባይነት የሌለዉ የሽያጭ ዉል በመፈራረም የነበረዉን ቤት አፍርሰዉ ሌላ ቤት በመስራታቸዉ ብቻ ይህ ተቀባይነት የሌለዉ ዉል እንዲፈርስ በፍርድ ቤት ክስ የማቅረብ መብትን የሚገድብ የህግ ምክንያት የሌለ ሲሆን ተጠሪዎች የአመልካችን ቤት አፍርሰዉ በይዞታዉ ላይ ሌላ ህንፃ መገንባታቸዉ የሽያጭ ዉሉ በህግ ፊት ተቀባይነት እንደሌለዉ ከተረጋገጠና ፈራሽ መሆኑ ፍርድ እና ዉሳኔ ካገኘ በኃላ ሊታይ የሚገባዉ ተዋዋይ ወገኖችን ወደ ነበሩበት የመመለስ ጉዳይ ሆኖ ሳለ ስር ፍርድ ቤት ኤርትራዊያንን ንብረት አስመልክቶ የወጣዉን መመርያ እና ፍታብሔር ስነስርአት ህግ ድንጋጌዎችን ከአላማው ዉጭ በመተርጎም የሰጡት ብይን እና ዉሳኔ መሰረታዊ ህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል፡፡ አመልካች ተጠሪዎች በቤቱ ላይ የሽያጭ ዉል መዋዋላቸዉን ያወቅሁ ህዳር ወር 2014 ዓ/ም ወደ ኢትዮጵያ የመግቢያ ቪዛ አግኝቸ ከተመለስኩ በኃላ ሆኖ ሳለ ተጠሪዎች ራሳቸዉ ምስክር ሆነዉ በመቅረብ የአመልካች ቤት በተሸጠበት ግዜ ስለ መሸጡ በስልክ ተነግሯታል በማለት የሰጡት የምስክርነት ቃል በፁሁፍ መልሳቸዉ ላይ ያላነሱት ሲሆን የምስክርነት ቃሉን የሰጡት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ተጠሪዎች ከመሆናቸዉ እና በዝምድና እና በጥቅም የተሳሰሩ ከመሆናቸዉ አንፃር እምነት የማይጣልበት ሆኖ ሳለ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ስለ ቤት ሽያጭ ዉል ታዉቅ ነበር በማለት ክሱን በይርጋ ተግዷል ተብሎ የተሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል ብለዋል።

ቅሬታው ተመርምሮ አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ በሰጡት ዉክልና በተጠሪዎች መካከል የተፈፀመዉ የሽያጭ ዉል በህግ ተቀባይነት የሌለዉ በመሆኑ እንዲፈርስላቸዉ ያቀረቡት አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች የክስ ምክንያት የለውም እንዲሁም በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት ዉድቅ የተደረገበትን አግባብ ከፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 33፣ 231 እንዲሁም በሰበር መ/ቁ 98177፣ 158255 ከተሰጡ ውሳኔዎች አንፃር ለመመርመር ሲባል ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀርቡ ተደርጓል።

የመልሱ ይዘት በአጭሩ በስር ፍርድ ቤት የቀረበው ክስ ይዘት 1ኛ ተጠሪ በውክልና እንዲያስተዳድሩ የያዙትን ቤት ባለቤታቸው ለሆኑት ለ2ኛ ተጠሪ ሸጠው ተገኝተዋል የሚል መሰረታዊ ይዘት ያለው ቢሆንም ተሸጠ የተባለው ቤት በአሁኑ ጊዜ ያለ ስለመሆኑ መነሻ ማስረጃ ያልቀረበ እና በስር ፍርድ ቤት አመልካች በክሱ የጠቀሱት ይዞታ በአሁኑ ወቅት አለመኖሩ የተረጋገጠ ከመሆኑ በተጨማሪ በወቅቱ በተወሰደው የመንግስት ውሳኔና እርምጃ መሰረት በቤቱና በይዞታው ላይ የተደረገውን የሽያጭ ውል እንዲፈርስ አመልካች ክስ የሚያቀርቡበት የሕግ መሰረት የለም። ቤትና ንብረቱ የአመልካች ነው ቢባል እንኳን አመልካች ንብረቱን እንዲያገኙ የሚፈቅድ የሕግ አግባብ የሌለ በመሆኑ ክሱ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2209 እና ሌሎች የውክልና ህግ ድንጋጌዎችን፣ እንዲሁም የወቅቱን የመንግስትን ውሳኔ፣ ግንቦት ወር 2001 ዓ/ም የወጣውን የሚኒስትሮች ምክር ቤት መመሪያ ያጣሰ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 231 መሰረት የክስ ምክንያት የለውም ተብሎ በስር ፍርድ ቤት መወሰኑ በአግባብ ነው። በሌላም በኩል አመልካች ስለሁኔታው ያወቅሁት ህዳር ወር መጨረሻ 2014 ዓ/ም ኢትዮጵያ ውስጥ ስገባ ነው በማለት ከይርጋ እገዳ ለማምለጥ በማሰብ ክሳቸው ላይ የጠቀሱ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ ለክሱ ምክንያት የሆነውን ቤት ለ2ኛ ተጠሪ የሸጥኩት ለአመልካች አሳውቄና ተስማምተንበት ስለመሆኑ የተረጋገጠ እና በዚህ ጭብጥ ላይ የቀረቡት ምስክሮች ህጉ በሚፈቅደዉ አግባብ የቀረቡ እና እንዳይመሰክሩ ህጉ ክልከላ የማያደርግ በመሆኑ የተሰሙትም የምስክሮች ቃል እጅግ ተዓማኒነት ያለው በምንም መልኩ በመስቀለኛ ጥያቄ ያልተስተባበለ በመሆኑ አመልካች የምስክሮቹን ዝምድና መሰረት በማድረግ የተሰጠ ነው በማለት ያቀረቡት ቅሬታ ተገቢነት የለዉም። አመልካች ያቀረቡት ምክንያት ይርጋን ለማቋረጥ የሚያስችል

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ህጋዊ ምክንያት አይደለም በ1991 ዓ/ም በተከሰተው የኢትዮ-ኤርትራ ግጭት ሁሉም ኤርትራዊ ኢትዮጵያ ውስጥ እንዳይገባ ለረዥም አመታት ተከልክሎ ነበር ለማለት የማይቻል እና በኢትዮጵያ ውስጥ ስላለው ንብረትም መረጃ ለማግኘት ፍጹም ክልከላ ነበር ለማለት አይቻልም፤ በተለይ ከ2001 ዓ/ም ጀምሮ ኤርትራዊያን በኢትዮጵያ ውስጥ ያላቸውን ንብረታቸውን ማግኘት እንደሚችሉ በመንግስት ተወስኖ ግልጽ መመሪያም ወጥቶ በስራ ላይ እያለ በ2010 ዓ/ም የሁለቱ ሀገራት ህዝቦች እንዲገናኙ የአገራቱ ድንበሮች ለሁለቱም አገራት ዜጎች ክፍት እንዲሆኑ በይፋ ታውጀና ወዲያውኑ ተግባራዊ ሁኖ ኤርትራዊያን ወደ ኢትዮጵያ መግባት የጀመሩ በመሆኑ አመልካች ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገቡ ልዩ ክልከላ ያልነበረባቸዉ በመሆኑ ከ2001 ዓ/ም ጀምሮ መብታቸውን ማስከበር ይችሉ ነበር፡፡ በመሆኑም ከ2001 ዓ/ም ጀምሮ ሲቆጠር ከፍተኛው የአስር አመት ይርጋም ሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2187(2) መሰረት ለጉዳዩ ቀጥተኛ አግባብነት ያለው የሁለት አመት ይርጋ የሚያግዳቸው በመሆኑ በዚህ ረገድ የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ብይን እና የከፍተኛው ፍርድ ቤት ያሳለፈው ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካችም የመልስ መልስ በማቅረብ ቅሬታዉን አጠናክረዉ ተከራክረዋል፡፡ መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረውም በዚህ ሁኔታ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን በበኩላችን የአመልካች አቤቱታ የክስ ምክንያት የሌለው ነው እንዲሁም በይርጋ የታገደ ነው ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን ዳኝነት አግባብነት ከግራቀኙ ክርክር ይዘትና ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ካላቸው የህጉ ድንጋጌዎች እንዲሁም አስቀድመው ከተሰጡ የሰበር ውሳኔዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደሚታወቀው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ በዋናው ህግ የተቀመጡትን መብትና ግዴታዎች ወደ ተግባር ለመለወጥ እንዲያስችል ታስቦ የተዘረጋ ስርዓት ነው፡፡ ከሳሽ የሆነው ወገን በከሳሽነት ተሰይሞ ክርክሩ እንዲቀጥል ለማድረግ አንደ ክርክሩ በማስረጃ አስደግፎ ቢያስረዳ ከህግ ወይም ከውል የመነጨ መብትና ግዴታ ያለ መሆኑን ለማመልከት በሚያስችል ደረጃ ክሱ ተዘጋጅቶ መቅረብ እንዳለበት ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33/2/ እና 33/3/ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ የእነዚህ ድንጋጌዎችን መስፈርት ያላሟላ ክስ ሲቀርብ ተከሳሾቹን እንኳ መጥራት እንደማያስፈልግ እና ክርክሩም በጅምር ደረጃ ሊቋረጥ እንደሚገባ ተገልፆ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 231/1/ሀ/ መደንገጉም ክርክሩ ውጤት ኖሮት በመሰረታዊ ህግ የተቀመጠውን መብትና ግዴታ ሊያስከብር መቻሉን ለማረጋገጥ ነው፡፡ በአንፃሩ ከሳሽ አንዳቀረቡት ክርክር በማስረጃ አስደግፈው ቢያስረዱ ከህግ ወይም

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ከውል የመነጨ መብትና ግዴታ ያለ መሆኑን ማሳየት ከተቻለ ክሱ የክስ ምክንያት የለውም የሚባልበትና በመቃወሚያ ውደቅ የሚደረግበት የህግ አግባብ አይኖርም፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች ክስ ያቀረቡት በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ምክንያት ከኢትዮጵያ ወደ ኤርትራ መወሰዳቸውን፤ በሄዱበት ወቅት በአ/አበባ ከተማ በቀድሞዉ አጠራር ወረዳ 20 ቀበሌ 51 በአሁኑ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወራዳ 05 የቤት ቁጥር 918 ተመዝግቦ የሚገኝ መኖርያ ቤታቸውን በተመለከተ ዉክልና ለ1ኛ ተጠሪ መስጠታቸውን፤ 1ኛ ተጠሪ ከእዉቅናቸው ዉጭ ቤቱን ለራሳቸው ባለቤት (ለ2ኛ ተጠሪ) በሽያጭ ያስተላለፉ መሆኑን በማረጋገጥ የሽያጭ ዉሉ ፈራሽ ነዉ ተብሎ እንዲወሰን ጠይቀዋል፡፡ ክሱን ይደግፋል የሚሉትን ማስረጃም ዘርዝረዋል፡፡ በዚህ መልኩ ተረጋግጦ የቀረበው የአመልካች አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 33/2/ እና 33/3/ እንደተደነገገው ከውል የመነጨ መብትና ግዴታ ያለ መሆኑን ለማመልከት የሚበቃ ክርክር እንዳቀረቡ አስረጂ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ደግሞ የግራቀኙ ዝርዝር ክርክር እና ማስጃቸው ታይቶ ውሳኔ ሊሰጥ ከሚገባ በቀር አመልካች መጠየቅ የሚችሉት በዝግ አካውንት የተቀመጠ የሽያጭ ዋጋ ከሚሆን በቀር ውሉ እንዲፈርስ ሊሆን አይችልም ተብሎ አመልካች በዳኝነት ጥያቄ ምርጫቸው ዉሉ እንዲፈርስ ያቀረቡት ጥያቄ የክስ ምክንያት የለዉም ተብሎ መወሰኑ የቀረበውን ክስ ይዘት እና ክርክሩ የሚመራበትን ሥነ ሥርዓት የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ሌላው በስር ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ያገኘው የመ/ደረጃ መቃወሚያ እና ለውሳኔ መሰረት የተደረገው የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ በይርጋ የታገደ ነው መባሉ ነው፡፡ ከመዝገቡ መረዳት እንደቻልነው አመልካች በተጠሪዎች መካከል የሽያጭ ውሉ በተደረገበት ወቅት በኢትዮጵያ አለመኖራቸው አከራካሪ አይደለም፡፡ በሌላ በኩል የስር ፍርድ ቤቶች ዉሉ የተደረገዉ ግንቦት 23 ቀን 1992 ዓ/ም መሆኑን፤ በፍ/ብ/ህ/ቁ 2187(1) መሰረት በዉክልና መነሻነት ሽያጭ ሲፈፀም ዉሉ ሊፈርስ የሚችለዉ ወካዩ (ሿሚዉ) ስለ ሽያጩ ካወቀበት ቀን ጀምሮ በሁለት አመት ዉስጥ የሽያጭ ዉሉ እንዲፈርስ ካልጠየቀ የዉል ይፍረስልኝ ጥያቄው በይርጋ የሚታገድ መሆኑን፤ አመልካች ሽያጩ እንደተፈፀመ ያወቅኩት ወደ ኢትዮጵያ በተመለስኩ ጊዜ ህዳር 14 ቀን 2014 ዓ/ም ነዉ ይበሉ እንጂ በተጠሪዎች ቤቱ ሲሸጥ እንዳሳወቋቸዉ የተሰጠውን ምስክርነት ያላስተባበሉ በመሆኑ ክሱ ውል ከተደረገ ከሁለት አመት በኃላ የቀረበ በመሆኑ በይርጋ ይታገዳል ብለዋል፡፡ ይሁንና የስር ፍርድ ቤቶች በኢትዮጵያ እና በኤርትራ መካከል የነበረው ግጭት የይርጋው ጊዜ መቆጠርን የሚያቋርጥ ስለመሆን አለመሆኑ ጉዳዩን ከዚህ አንጻር በአግባቡ ሊመረምሩ ይገባ ነበር፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በስር ፍርድ ቤቶች እንደተገለፀው ውል እንዲፈርስ በአመልካች ክሱ የቀረበው በ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች መካከል ውል ከተደረገበት ቀን ጀምሮ በህጉ ተመለከተው ጊዜ ካለፈ በኋላ ቢሆንም አመልካች ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሱ በኋላ ክስ ባለማቅረባቸው የይርጋው ጊዜ ማለፉን በመጥቀስ ወይም ውሉን በመቃወም ክስ ሊያቀርቡ የሚችሉበት ሌላ ሁኔታ የነበረ ስለመሆኑ በማረጋገጥ ውሳኔ አልተሰጠም፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በመንግስት መመሪያ ከሃገር እንዲወጡ ተደርገው የነበሩ ኤርትራዊያንን በተመለከተ ከኢትዮጵያ ከወጡ ጀምሮ ተፈቅዶላቸው እስከተመለሱ ድረስ ያለው ጊዜ በይርጋው ውስጥ ሊታሰብ የሚችልበት የህግ አግባብ እንደማይኖር ይህ ሰበር ችሎት የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845 እና 1846 ድንጋጌዎችን በመተርጎም በሰበር መዝገብ ቁጥር 92408፣ 98177፣ 158255 እና በሌሎችም መዛግብት አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠ ሲሆን ይኸው ትርጉም በህጉ አግባብ እስካልተለወጠ ድረስ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 መሰረት በተያዘውም ጉዳይ ላይ ተፈጻሚነት የሚኖረው ነው፡፡ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ይህን ወደጎን በማለት የሰጡት ውሳኔ ተገቢነት የለውም ብለናል፡፡

በአጠቃላይ የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች ውል ይፍረስ በሚል ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ የክስ ምክንያት የለውም፤ እንዲሁም ክሱ በይርጋ የታገደ ነው በማለት የደረሱበት መደምደሚያ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 179184 ነሐሴ 10 ቀን 2014 ዓ/ም ያሳለፈዉ ብይን እና ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 297146 የካቲት 13 ቀን 2015 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተዘጋውን መዝገብ አንቀሳቅሶ በፍሬ ጉዳዩ ረገድ የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት ተገቢውን እንዲወስን ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 341(1) መሰረት መልሰናል፡፡ የውሳኔው ግልባጭ ይድረሰው፡፡
3. ዕግድ ካለ ተነስቷል፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ስላስከተለው ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ/ጋ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መዝገብ ቁጥር - 247284

ቀን - 05/02/2017

ዳኞች፡- ሽመክት አሰፋ

ገበየሁ ፈለቀ

አለማየሁ ሹናራ

ተናኜ ጥላሁን

ዘውዲቱ ታደሰ

አመልካች - ወ/ሮ ሄለን ገ/ማርያም -ጠበቃ አቶ ጌታቸው ውብሸት -ቀረበ

ተጠሪዎች -1. ለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ አስተዳደር } አልቀረቡም

2. ለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 አስተዳደር

መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው ለምርመራ ስለሆነ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የተጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን በስር ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪዎች ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የከሳሽ ክስ ይዘት በአጭሩ ስፋቱ 2,220 ካሬ ሜትር ይዞታና ቤት ለልማት ለናይል ፔትሮሊየም ኩባንያ ተሰጥቷል፡፡ ካሳና ምትክ ቦታ አልተሰጠኝም ምትክ ቦታና ካሳ እንዲሰጠኝ የቦሌ ክፍለ ከተማ ዋና ስራ አስፈፃሚ ፅ/ቤት በ 25/09/2007 ኢ.ም ያሳወቀ ቢሆንም ምላሽ አልሰጡም፡፡ በመሆኑም ተከሳሾች ባለባቸው

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አስተዳደራዊ ኃላፊነት መሰረት ምትክ ቦታ እና ካሳ ሊሰጥ ይገባል ወይስ አይገባም በሚለው ላይ ውሳኔ እንዲሰጡ እንዲወሰን የሚል ነው። የስር ተከሳሾች የበኩላቸውን መልስ በፅሁፍ የሰጡ ሲሆን ይዘቱ በአጭሩ በመልሳቸው ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ ላይ ለከሳሽ ምትክ ቦታና ካሳ እንዲሰጥ ብሎ ለመወሰን በአዋጅ ቁጥር 361/1995 እና አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሰረት ስልጣን ለፍርድ ቤት አልተሰጠውም። አቤቱታው ሊቀርብ የሚችለው በአዋጅ ቁጥር 1183/2011 መሰረት ለአስተዳደር አካሉ እንጂ ለፍርድ ቤት ባለመሆኑ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ለመወሰን ስረ ነገር ስልጣን የለውም በማለት ተቃውመዋል። ከሳሽ ለክሱ መቃወሚያ የሰጠው መልስ በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀፅ 40(1)(ለ) መሰረት ፍርድ ቤት ስልጣን አለው። የከተማው አስፈፃሚ አካላት ኃላፊነታቸውን ባልተወጡ ጊዜ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ የሚቀርብ ክስ የመዳኘት ስልጣን አለው። የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 99375 እና 48217 መሰረት አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሰረት ፍርድ ቤቱ ስልጣን ስላለው መቃወሚያ ውድቅ እንዲደረግ በማለት ተከራክራለች የቃል ክርክር ተሰምቷል። የግራ ቀኙ የፅሁፍና የቃል ክርክር ከተጠናቀቀ በኃላ ፍርድ ቤቱ መዝገቡን መርምሮ ከሳሽ ያቀረባቸው የፅሁፍ ማስረጃዎች ለከሳሽ ምትክ ቦታና ካሳ ሊሰጣቸው እንደሚገባ የተወሰነ ሲሆን በአስተዳደር አካላት ውሳኔ መሰረት መፈፀም ሲገባ ያልፈፀሙት አካላትን ለይተው መጠየቅ ሲኖርባቸው ተከሳሾች ምትክ ቦታ እና ካሳ እንደሚገባኝ ወይም እንደማይገባኝ ይወሰንልኝ በማለት ያቀረቡት ክስ መክሰስ በሌለባቸው ተቋማት ላይ የቀረበ ክስ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ተከሳሾች ያቀረቧቸውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መሰረት ክሱን ውድቅ አድርጓል።

አመልካች በዚህ ብይን ላይ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ቅሬታ ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርባለች። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 37791 በቀን 16/02/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት ለህዝብ ጥቅም ሲባል የመሬትን ይዞታ የሚለቅበት ካሳ የሚከፈልበት እና ተነሺዎች መልሰው የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1161/2011 አንቀፅ 18(1) መሰረት በምትክ ቦታ እና ካሳ አሰጣጥ ጋር በተያያዘ የሚነሱ ጉዳዮች መታየት ያለባቸው ለአቤቱታ ሰሚ አካልና ለይግባኝ ሰሚ ጉባኤ መቅረብ እንዳለበት ተደንግጎ ይገኛል። ጉዳዩን በይግባኝ የሚያየው መደበኛ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 1161/2011 አንቀፅ 20(2) ላይ ተደንግጎ ይገኛል። የአሁኑ ክርክር ምትክ ቦታና ካሳ ሊሰጠኝ ይገባል የሚል በመሆኑ የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን አይተው ለመወሰን የሚያስችል የዳኝነት የስረ ነገር ስልጣን የላቸውም በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን ሽሮታል።

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አመልካች ሰበር ቅሬታ ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኝም፡፡ የአሁን ሰበር ቅሬታ የቀረበው አመልካች በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት ነው፡፡ አመልካች በ 14/09/2015 አ.ም በ 04 ገፅ ሰበር ቅሬታ አቅርባለች፡፡ የሰበር ቅሬታውም ይዘት በአጭሩ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ክስ ምክንያት አለው ምክንያቱም ለክርክሩ መነሻ በሆነው ሀብት ላይ መብትና ጥቅም መኖሩን የሚያስረዳ የሰነድ ማስረጃ አቅርቢያለሁ፡፡ የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ አመልካች ፍትህ የማግኘት መብት የሚጥስ ውሳኔ ነው፡፡ ክስ የቀረበውም መክሰስ የሚገባቸው ተቋማት ላይ ነው፡፡ የመኖሪያ ቤቴን ከነይዞታው ለልማት በሚል በጉልበት ወስደው ለሌላ ድርጅት የሰጡት ተከሳሾች ናቸው፡፡ የ 1ኛ መልስ ሰጪ አካላት (Department) የሆኑት ክፍሎች ለከሳሽ ችግር መፍትሄ እንዲሰጥ የውሳኔ ሀሳብ ማቅረባቸው ለክሱ ምክንያት በሆነው ጉዳይ ላይ ውሳኔ መስጠቱን እና የቀረበው የአፈፃፀም ጉዳይ መሆኑን አያሳይም፡፡ ስለዚህ የስር ፍርድ ቤት ያልፈፀሙ አካላትን ለይተው መክሰስ አለባቸው በማለት መዝገቡን መዝጋቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፡፡

የአመልካች ጥያቄ ለልማት በሚል ሰበብ ቦታዬን ሲወስድ በቦታው ላይ ያለው ይዞታ ህጋዊ ማስረጃ ካለ ካሳ ሊከፈለው ይገባል ወይስ አይገባም የሚለውን አስተዳደራዊ ውሳኔ አልሰጡኝም የሚል ነው እንጂ ካሳና ምትክ ቦታ ይሰጠኝ የሚል ጥያቄ ባለመሆኑ የአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ስረ ነገር ስልጣን ያለው በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ተሸሮ አጣሪ ኮሚቴ አጣርተው በቀረበው የውሳኔ አስተያየት መሰረት ይዞታን በተመለከተ አመልካች ያቀረበው ሰነድ ማስረጃ ትክክል ከሆነ ካሳና ምትክ ቦታ ይገባል፡፡ ሰነድ ማስረጃ ትክክል ካልሆነ ካሳና ምትክ ቦታ አይገባም ብለው ተጠሪዎች እንዲወስኑ እንዲያርምልኝ የሚል ነው፡፡ ሰበር ችሎት በ 27/07/2016 አ.ም በዋለው ችሎት

1. ተጠሪዎች ተገቢውን ማጣራት በማድረግ ካሳና ምትክ ቦታ ሊሰጠኝ የሚገባ መሆን አለመሆኑን በሚመለከተው አስተዳደራዊ ውሳኔ ለመወሰን ፍቃደኛ ስላልሆኑ አስተዳደራዊ ኃላፊነታቸውን በመወጣት ለአመልካች ምትክ ቦታና ካሳ ሊሰጥ የሚገባ መሆን አለመሆኑን በተመለከተ ውሳኔ እንዲሰጡ ይወሰንልኝ በሚል ዳኝነት ክስ የመዳኘት ስልጣን ያለው ማን ነው?
2. ዳኝነት መጠየቅ ያለበት በቀጥታ ክስ መልክ ነው ወይስ በአስተዳደራዊ ስነ ስርአት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 ላይ በተደነገገው አግባብ ነው?
3. በዚህ መልክ የሚቀርብ ክስ በፍርድ ሊታይ የሚችል ነው ወይስ አይደለም?

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

4. በክሱ የተጠቀሰው ምክንያት ተጠሪዎችን የማያስከስስ ነው ወይስ አይደለም?

የሚሉትን ለማጣራት ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪዎች በ 19/09/2016 ዓ.ም 03 ገፅ መልስ አቅርበው ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡ ይዘቱ በአጭሩ ፍርድ ቤት ጉዳዩን መዳኘት እንዳለበት በመርህ ደረጃ ህገ መንግስቱ የሚደነግግ ቢሆንም በልዩ ሁኔታ ጉዳዩን እንዲዳኝ ለሌላ አካል የተሰጠ ጉዳይ ፍርድ ቤት የመዳኘት ስልጣን የለውም፡፡ ፍርድ ቤቱ አንደ የልማት ተነሺ ነኝ ለሚል ሰው ካሳ ሊሰጥ ይገባል ወይስ አይገባም ብላቹሁ ወስኑ በሚል ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 361/1995 ም ሆነ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ስልጣን አልተሰጠውም፡፡ በአዋጅ ቁጥር 1183/2012 መሰረት ይህ ጉዳይ ሊቀርብ የሚገባው ለአስተዳደር ነው እንጂ ለፍርድ ቤት አይደለም፡፡ በአዋጅ ቁጥር 74/2014 አንቀፅ 24 ላይም ስልጣኑ የፍርድ ቤት ሳይሆን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ልምት ማኔጅመንት ቢሮ ነው፡፡ ቢሮው ውሳኔ ለመስጠት ዳተኛ ከሆነ ጉዳዩ አቤቱታ መቅረብ ያለበት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ከዚህ አንፃር አዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 74/2014 ይዞታ አሰጣጥ መመሪያ 12/2004 ለህዝብ ጥቅም ሲባል መሬት ስለሚለቀቅበት ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 1161/2011 ካሳና ምትክ ቦታ የመስጠት ስልጣን የተሰጠው ለመሬት ልማት ማኔጅመንት ቢሮ ነው እንጂ ለተጠሪዎች አልተሰጠም፡፡ ስለዚህ የስር ፍርድ ቤቶች በየደረጃው የሰጠው ብይንና ፍርድ የሚነቀፍ ባለመሆኑ እንዲፀናልኝ የሚል ነው፡፡ አመልካች በ 06/10/2016 ዓ.ም በ 06 ገፅ የሰበር ቅሬታ በማጠናከር አቅርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ በተገለፀው መሰረት በመጠቃለሉ እኛም ለሰበር ቅሬታ መነሻ የሆነው የሁለቱ ፍርድ ቤቶች ብይንና ፍርድ በግራ ቀኙ በኩል ክርክር በሰበር የተያዘው ማስቀረቢያ ጭብጥ አግባብነት ካላቸው ህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ሰበር ችሎት በሚያቀርብበት ጊዜ የያዘው ጭብጥ እንደተጠበቀ ሆኖ በተጨማሪ የአመልካች ዳኝነት ጥያቄ ለመወሰን የስረ ነገር ስልጣን ያለው የፌዴራል ፍርድ ቤት ነው ወይስ አዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው የሚሉትን ጭብጥ በተጨማሪ በመያዝ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ መርምረን እንደተረዳነው ከሆነ የአመልካች ዳኝነት ጥያቄ ይዞታቸው በልማት ምክንያት ስለተወሰደባቸው ካሳና ምትክ ቦታ እንዲሰጣቸው የቦሌ ክፍለ ከተማ ዋና ስራ አስፈፃሚ ቢወስንም ተጠሪዎች መልስ ስላልሰጡ ካሳና ምትክ ቦታ ሊሰጠኝ ይገባል ወይም አይገባም ብለው ተጠሪዎች እንዲወስኑ ብለው ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲሰጥ በማለት ነው፡፡ ለህዝብ ጥቅም ሲባል

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበት፣ ካሳ የሚከፈልበት እና ተነሺዎች መልሰው የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1161/2011 ላይ ህጋዊ የመሬት ባለቤት ለህዝብ ጥቅም ሲባል መሬቱን ሲለቅ ካሳና ምትክ ቦታ ሊሰጥ እንደሚገባ በአዋጅ ውስጥ በግልፅ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄም ይዞታቸው ለልማት ስለተወሰደ ምትክ ቦታና ካሳ አልተሰጠኝም የሚል ነው፡፡ ይዞታው ለህዝብ ጥቅም ሲወሰድ ካሳና ምትክ ቦታ አከፋፈልና አሰጣጥ ስነ ስርአት በአዋጅ ቁጥር 1161/2011 አንቀፅ 17 መሰረት በካሳ ገማች ኮሚቴ ንብረቱ ይገመታል፡፡ በካሳ ገማች ኮሚቴ የተገመተው ግምት ላይ ቅሬታ ያለው ወገን ቅሬታውን ለአቤቱታ ሰሚ አካል ማቅረብ እንደሚቻል በአዋጅ አንቀፅ 19(1) ስር ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ጉባኤው በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ውሳኔው በፅሁፍ ከደረሰው ቀን ጀምሮ በ 30 ቀን ውስጥ ይግባኝ ለክልል ከፍተኛው ፍርድ ቤት በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ከተሞች ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ማቅረብ እንዳለበት በአዋጅ ቁጥር 1161/2011 አንቀፅ 20(2) ስር ተደንግጓል፡፡ አሁን የያዝነው ጉዳይ የካሳና ምትክ ቦታ ጥያቄ ጉዳይ ስለሆነ የካሳ አከፋፈል እና ምትክ ቦታ አሰጣጥ ከላይ በተገለፀው አዋጅ መሰረት የሚፈፀም ሲሆን አመልካች ካሳና ምትክ ቦታ እንዲሰጣቸው ለቦሌ ክፍለ ከተማ ዋና ስራ አስፈፃሚ አመልክተው የቦሌ ክፍለ ከተማ ዋና ስራ አስፈፃሚ ካሳና ምትክ ቦታ ሊሰጣቸው እንደሚገባ ውሳኔ የሰጠ ቢሆንም ተጠሪዎች መልስ አልሰጡም ስለዚህ ካሳና ምትክ ቦታ ሊሰጣቸው ይገባል ወይስ አይገባም የሚለው ውሳኔ ተጠሪዎች እንድሰጡ ተብሎ እንዲወሰን የሚል ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ካሳና ምትክ ቦታ ሊሰጣቸው እንደሚገባ የቦሌ ክፍለ ከተማ ዋና ስራ አስፈፃሚ ስለወሰነ ድጋሚ ተጠሪዎች ካሳና ምትክ ቦታ ሊሰጣቸው ይገባል ወይስ አይገባም ብሎ መወሰን አስፈላጊ አይደለም፡፡ በቦሌ ክፍለ ከተማ ዋና ስራ አስፈፃሚ ውሳኔ መሰረት ካሳና ምትክ ቦታ የመስጠት ስልጣን ያለው አካል ከልክሎ ከሆነ ካሳና ምትክ ቦታ እንዲሰጥ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ክስ ማቅረብ አለባቸው፡፡

አመልካች ካሳና ምትክ ቦታ ሊሰጣቸው ይገባል ወይስ አይገባም ብለው ውሳኔ ተጠሪዎች እንዲሰጡ መጠየቅ አይጠበቅም ምክንያቱም የአመልካች ይዞታ ለልማት የተወሰደባቸው መሆኑን አምኖ የቦሌ ክፍለ ከተማ ዋና ስራ አስፈፃሚ ካሳና ምትክ ቦታ ይሰጣቸው ብሎ የወሰነ ስለሆነ አመልካች በዚህ ውሳኔ መሰረት ካሳና ምትክ ቦታ መስጠት ስልጣን ያለውን አካል ካሳና ምትክ ቦታ እንዲሰጣቸው መጠየቅ ካልሰጠ በአዋጅ ቁጥር 1161/2011 አንቀፅ 20(2) መሰረት ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቅሬታ ማቅረብ አለባቸው ከላይ በተገለፀው መሰረት ይዞታቸው ለልማት ስለተወሰደባቸው ከካሳና ምትክ ቦታ አሰጣጥ ጋር የተያያዘ ጉዳይ የመዳኘት ስልጣን ያለው

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የፌዴራል ፍርድ ቤት ነው እንጂ የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን ያላቸውም በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 5(1)(ደ) ስር ለአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን አልተሰጠም፡፡ ከዚህ አንፃር የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን የለውም በማለት የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰጠው ፍርድ የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነም፡፡

ሲጠቃለል የምትክ ቦታና ካሳ ጥያቄ ጋር የተያያዘ ጉዳይ ክስ ሊቀርብ የሚገባው በፌዴራል ፍርድ ቤት ነው እንጂ አዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤት ስላልሆነ ለአመልካች ካሳና ምትክ ቦታ ሊሰጣቸው ይገባል ተብሎ በቦሌ ክፍለ ከተማ ዋና ስራ አስፈፃሚ የተወሰነ ጉዳይ በመሆኑ ተጠሪዎች በድጋሚ የሚወስኑበት ምክንያት ባለመኖሩ በስራ አስፈፃሚ ውሳኔ መሰረት ካልተፈፀመ አመልካች ስልጣን ባለው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክስ የማቅረብ መብታቸውን የሚከለክል ነገር ባለመኖሩ የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም ብለናል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል -

## ውሳኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 37791 በቀን 16/02/2015 አ.ም የሰጠው ፍርድ እና የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 39609 በቀን 13/06/2015 አ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስላልሆነ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስነ ስርአት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9(1)(ሀ) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠ እግድ ካለ ተነስቷል፡፡

## ትዕዛዝ

- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ም

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የሰበር መ/ቁ 247348

ጥቅምት 5 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች፡ ብርሃኑ አመነው

በእውቀቱ በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ብርሃኑ መንግስቱ

ማርታ ተካ

አመልካች ፡- ወ/ሮ ገነት ጉታ - ቀረቡ

ተጠሪ ፡- አቶ ወርቁ ደሜ - ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

መዝገቡ ለሰበር ችሎት የቀረበዉ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ የህግ ስህተት የለዉም በማለት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 423641 ላይ በቀን 08/09/2015ዓ.ም የሰጠዉ ትእዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት በሰበር ችሎት እንዲታረም ሲሉ አመልካች በቀን 15/09/2015ዓ.ም ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ ነዉ፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ሲታይ ተጠሪ የስር ከሳሽ ሲሆን በሰበር ክርክር ያልተሰየሙት አቶ ባልቻ ደሜ ተከሳሽ በመሆን ክርክር አድርገዉ ፍርድ ከተሰጠ በኂላ አመልካች የመቃወም አመልካች በመሆን የክርክሩ ተካፋይ ነበረች፡፡አመልካች በቀን 10/8/2014ዓ.ም ባቀረበችው የመቃወሚያ አቤቱታ በሀንቀሎ ዋቤ ወረዳ ካራሊሙ ቀበሌ ውስጥ የሚገኘው አዋሳኞቹ በክሱ የተጠቀሰው ይዞታ በጋብቻ ውል የተቆረጠልኝና ከ23 ዓመት በላይ ከእጄ ሳይወጣ ስጠቀምበት የነበረ ሲሆን ተጠሪ እና የስር ፍርድ ቤት ተከሳሽ ተሰማምተው እኔ ሳልሰማ ተከራክረው ውሳኔ የተሰጠ መሆኑን ከአፈፃጸም መ/ቁ/14280 የተገነዘብኩ ስለሆነ የአፈፃጸም መዝገቡ ታግዶ ይዞታዬ ከክርክሩ እንዲወጣልኝ በማለት የጠየቀች መሆኑን መዝገቡ ያሣያል፡፡

ተጠሪም በሰጠዉ ምላሽ የመቃወም አመልካች በከሳሽ እና በተከሳሽ መካከል ይደረግ የነበረውን ክርክር አመልካች ታወቅ ስለነበር ይህንን መቃወሚያ ልታነሳ አትችልም፤ማስረጃም አላቀረበችም፣ሚች ባለቤቷ ሌላ ሁለት ገመድ መሬት ቆጥሮላታል፤አከራካሪው መሬት ለእኔ የሚደርሰኝ ስለሆነ የተሰጠው ውሳኔ እንዲፀናልኝ በማለት የተከራከረ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የግራቀኙን ክርክር ከሰማና ምስክር አስቀርቦ ከመረመረ በኃላ የአመልካች ምስክሮች ይዞታው ለአመልካች በሰማኒያ መቆረጡን እንደመሰከሩ ጠቅሶ በሰበር መ/ቁ 107840 (ቅፅ 18) በተሰጠ ዉሳኔ መሰረት ይዞታው ባልና ሚስት ሲጋቡ የተሰጠና ሲጠቀሙበት የነበረ በመሆኑ የጋራ ንብረት ነዉ በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 360(2) መሰረት ከክርክሩ እንዲወጣ ሲል ወስኗል፡፡

ተጠሪ ውሳኔውን ተቃውሞ ይግባኝ ለአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ችሎቱ የስር ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔን በማፅናቱ ቅሬታውን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ችሎቱ አመልካች ከስር 1ኛ ተከሳሽ ጋር የነበራቸው ጋብቻ ፀንቶ ባለበትና ስለመለያየታቸው ማስረጃ በሌለበትና ክርክሩ እስከ ኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ደርሶ ባለበት የስር ተከሳሽ ከተጠሪ ጋር የነበራቸውን ክርክር አላዉቅም ማለቷ አሳማኝ አይደለም፤የአመልካች ምስክሮች ባልና ሚስት መሆናቸውን እናውቃለን፤የመጀመሪያውን ክርክር ማወቅ አለማወቋን አናውቅም ሲሉ መመስከራቸው ሎጂካል አይደለም፤ባልና ሚስት ሆነው ክርክሩን ይደባበቃሉ ተብሎ አይታሰብም በማለት አመልካች ክርክሩን እያወቀች የመጨረሻውን ውሳኔ ጠብቃ ያቀረበችዉን አቤቱታ የስር ፍርድ ቤት ውድቅ ማድረግ ሲገባው አቤቱታውን መቀበሉ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 358 መሰረት ያደረገ አይደለም ሲል የስር ወረዳ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የአመልካችን አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/360(2) መሰረት ውድቅ አድርጓል፡፡አመልካች ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ብታቀርብም በይግባኝ ሰሚው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

መሰረታዊ የህግ ስህተት አልተፈፀመም ሲል አቤቱታውን በአዋጅ ቁጥር 216/2011አንቀፅ 26(1) መሰረት ውድቅ አድርጎ ወስኗል፡፡ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ነዉ፡፡

አመልካች ግንቦት 15 ቀን 2015ዓ.ም ባቀረበችው የሰበር አቤቱታ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ ጉዳዩን ሲመለከት በስር ፍርድ ቤት የታለፈ ማስረጃ ካለ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 327 በማስረጃ ሳያጣራ በሰ/መ/ቁ/56795 (ቅፅ 12) ላይ የተሰጠውን ውሳኔ መሰረት አድርጎ አመልካች በወቅቱ በቦታው እንዳልነበረችና ከስር ተከሳሽ (ባለቤቷ) ጋር ተጣልታ እንደነበር በስር ፍርድ ቤት የቀረቡት የግራቀኙ ምስክሮች ያረጋገጡ ሲሆን የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምስራቅ ችሎትና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሻለና አዲስ ማስረጃ ሳይኖር የስር ወረዳና ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔን መሻራቸው መሰረታዊ ህግ ስህተት ስለሆነ ውሳኔያቸው ተሽሮ የሀንቆሎ ዋቤ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/13653 የሰጠው ውሳኔ እንዲፀናልኝ በማለት አመልክታለች ፡፡

የሰበር ችሎቱ አቤቱታውን ከመረመረ በኃላ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ቀደሞ ክርክር ሲደረግ ታወቅ ነበር በሚል የደረሰበትን ድምዳሜ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/358 ኣላማና አተገባበር ጋር እንዲሁም በመ/ቁ/56795 እንዲሁም በሌሎች መዝገቦች ላይ ከተሰጠው የህግ ትርጉም ጋር አገናዝቦ ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ተጠሪ በቀን 05/6/2016ዓ.ም ጽፎ ባቀረበዉ መልስ አመልካች የተሰጠኝን መብት ሆነ ብላ ለማሳጣት ከባለቤቷ ጋር ተማክራ ያቀረበችው አቤቱታ ነው፤ከባለቤቷ (ከስር ተከሳሽ) ጋር በነበረን ክርክር ይዞታው ጋብቻ በምንፈፅመበት ጊዜ ለአመልካች የተሰጣት ነው ብሎ ያነሳው ጥያቄም ሆነ ክርክር የለም፤መሬቱ በጋብቻ ጊዜ ያልተሰጣት፤አንድም ቀን ይዘውትም ሆነ አስተዳድረውት አያውቁም፤በእርሻም አልተጠቀሙም፤ይዞታው በስጦታ አልተሰጣትም እንጂ ቢሰጣት እንኳን ከ1991 እስከ 2016 ዓ.ም ድረስ 25 ዓመት ስለሚሞላ ይርጋ ያግደዋል፤በመሆኑም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት የለበትም ተብሎ እንዲፀና በማለት ተከራክሯል፡፡አመልካች አቤቱታዋን የሚያጠናክር የካቲት 18ቀን 2016 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርባለች፡፡

የክርክሩ አመጣጥ እና የግራቀኙ ክርክር ከላይ ባጭሩ የተመለከተው ሲሆን እኛም ያስቀርባል ሲባል የተያዘውን ጭብጥ ከግራቀኙ ክርክር፤በስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ እና ከተገቢው የህግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡እንደመረመርነዉ የሰበር ችሎቱ ዉሳኔ የሚሻዉ ጭብጥ በተጠሪ እና በስር ተከሳሽ (የአመልካች ባለቤት) መካከል ክርክር ተደርጎ ዉሳኔ ከተሰጠ በኋላ አመልካች በፍ/ብ/ስ/ስ ህግ ቁጥር 358 መሰረት ያቀረበችዉ መቃወሚያ ክርክር መኖሩን አታዉቅም

ነበር አይባልም ሲል የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ ላይ የተፈጸመ የህግ ስህተት አለ ወይ የሚለዉ ነዉ፡፡

በክርክሩ ተካፋይ ያልሆነ ወገን ባልተሳተፈበት ክርክር ተድርጎ መብቱን የሚነካ ፍርድ መሰጠቱን ባወቀ ጊዜ ፍርዱን በመቃወም መብቱን ማስከበር እንደሚችል በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ 358 ላይ ተደንግጓል፡፡ይሁንና ይህንን መብት በመጠቀም ረገድ ክርክሩ መኖሩን እያወቀ በቸልተኝነቱ ወይም በእሱ ጉድለት የክርክሩ ተካፋይ ሳይሆን የቀረ ወገን ከቅን ልቦና ዉጪ ጉዳዩን ለማጓተት የሚያቀርበዉ መቃወሚያ ተቀባይነት ሊኖረዉ እንዳማይገባ ሰበር ችሎቱ ገዥ ዉሳኔ የሰጠበት መሆኑ ይታወቃል(ሰበር መ/ቁ/56795፣40229፣93987 እና ሌሎች መሰል መዝገቦችን ይመለከታል)፡፡ከዚህ አኳያ የተያዘዉ ጉዳይ ሲታይ ቀደም ሲል የአመልካች ባል እና ተጠሪ ሲከራካሩ አመልካች በወቅቱ ከባለቤቷ ጋር ባለመግባባት ተለያይተዉ እንደነበር ጠቅሳ ክርክሩ መኖሩን እንደማታዉቅ የተከራከረች ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ ክርክር መኖሩን እያወቀች ጣልቃ ገብታ መከራከር እየቻለች ዉጤቱን ጠብቃ የመቃወም አቤቱታ ማቅረቧ ተገቢ አይደለም በማለት አጥብቆ ተከራክሯል፡፡

ስለሆነም አመልካች ክርክሩ መኖሩን ታዉቅ ነበር ወይስ አልነበረም ወይም ክርክሩ መኖሩን እያወቀች ጣልቃ ገብታ መከራከር ሲትችል ከቅን ልቦና ዉጪ ዉጤቱን ጠብቃ ያቀረበችዉ አቤቱታ ነዉ የሚለዉን ለመወሰን በእርግጥም የመቃወም አመልካች ቀደም ሲል ክርክር ሲደረግ የነበረ መሆኑን ክርክሩም የእሷን መብት የሚመለከት መሆኑን ታዉቅ እንደነበር መረጋገጥ ያለበት ፍሬነገር ጉዳይ ነዉ፡፡በዚህ ረገድ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለዉሳኔ መሰረት ያደረገዉ ምክንያት አመልካችና ስር ተከሳሽ ባልና ሚስት ሆነዉ አይነጋገሩም ወይም ክርክሩን አያዉቁም ተብሎ አይገመትም የሚል (መነሻ) ግምት በመያዝ እንጂ በማስረጃ በማጣራት አላረጋገጠም፡፡ከላይ እንደተገለጸዉ የአመልካች ዋነኛ መከራከሪያ ስር ከሳሽ(አሁኑ ተጠሪ) እና ስር ተከሳሽ (ባለቤቷ) ሲከራከሩ ከባለቤቷ ጋር ፍቺ ሳይፈጸም ነገር ግን ባለመግባባት ተለያይተን ሲንኖር ነበር በሚል ምክንያት ክርክር መኖሩን አላዉቅም የሚል ነዉ፡፡ስለሆነም ፍቺ ባይኖር እንኳን ተለያይተዉ ይኖሩ ነበር ወይስ አልነበረም?ክርክር መኖሩን ታዉቃለች ወይስ አታዉቅም የሚሉና ተያያዥ ጥያቄዎች በማስረጃ ነጥሮ መወሰን አለበት፡፡ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ይህንኑ በማስረጃ ሳያጣራ ተከሳሽ እና አመልካች ባልና ሚስት ነበሩ ከሚል መነሻ ክርክር መኖሩን ተዉቃለች የሚል ድምዳሜ ላይ መድረሱ የአመልካችን የመሰማትና የመከራከር ህገ መንግስታዊ መብት የሚጻረር ነዉ፡፡የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በተለያዩ መዝገቦች በሰጠዉ ገዥ ዉሳኔ እንዳመለካተዉ በማስረጃ ነጥሮ መወሰን የሚገባ ፍሬነገር ጉዳይ በአግባቡ ሳይጣራ የሚሰጥ ፍርድ የክርክር አመራር ጉድለት ያለበት እና ሚዛናዊ ፍትህ የማግኘት መብት የሚጎዳ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህትት የተፈጸመበት ነዉ ተብሎ በሰበር ችሎቱ ሊታረም የሚገባ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ሰበር መ/ቁ/43845፣37105 እና ሌሎች መዝገቦችን ይመለከቷል።እንደሚታወቀው አንድ ጉዳይ በሰበር ችሎት ሊታይ የሚችለው የመጨረሻ ዉሳኔ ያገኘ ሆኖ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4) እና አንቀጽ 10 ስር ከተመለከቱት የህግ መመዘኛ አንዱን ወይም ከአንድ በላይ ድንጋጌ አሟልቶ ሲገኝ ነው፡፡በተለይም በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ /ትዕዛዝ/ ብይን ሲሆን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታዉን ተቀብሎ በሰበር የማየት ስልጣን የሚኖረዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ የሚቃረን ሲሆን እንዲሁም አግባብነት የሌለዉን ህግ በመጥቀስ ወይም ህግን ያላግባብ በመተርጎም የተሰጠ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሆኖ ጉዳዩም አገራዊ ፋይዳን የሚመለከት ሲሆን ብቻ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 10 (1/ሐ/ እና /መ) ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡

ስለሆነም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች ክርክር መኖሩን ታወቅ ነበር ወይስ አልነበረም የሚለዉን አመልካች ካቀረበችዉ ክርክር አኳያ ተገቢዉን ጭብጥ በመያዝ በስር ፍርድ ቤት የተሰሙ ማስረጃዎች ይዘት ሳይመረምር ወይም አስፈላጊ ሆኖ ካገኘዉ አግባብነት ያላቸዉን ማስረጃዎች በተሟላ ሁኔታ ሳይሰማ እና ሳይመረመር ግምት ላይ ተመስርቶ ስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ መሻሩም ሆነ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ይህንኑ ሳያርም ማለፉ ስለጭብጥ አመሰራረት ማስረጃ አቃባበል እና ክርክር አመራር ስርዓት ሰበር ችሎቱ የሰጠዉን ገዥ ዉሳኔ የሚቃረን በመሆኑ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4ሐ ና ሸ) እና 10(1/ለ) መሰረት መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ብለናል፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ዉሳኔ</u>

1ኛ/በዚህ ጉዳይ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 416831 ቀን በቀን 25/08/2015ዓ.ም ዉሳኔ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በመ/ቁ/423641 ላይ በቀን 08/09/2015ዓ.ም የተሰጠዉ ትእዛዝ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስነስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1) መሰረት ተሸሯል፡፡

2ኛ/የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መዝገቡን በማንቀሳቀስ ከላይ በፍርድ ሀተታ ላይ በተገለጸዉ እና ተያያዥ ጭብጥ ላይ ግራቀኝ በማከራከርና አግባብነት ባለዉ ማስረጃ በማጣራት ተገቢዉን እንዲወስን በማለት መዝገቡን በሰበር ስነስርዓት መመሪያ አንቀጽ 9(2) መሰረት መልሰንለታል፡፡ይጻፍ

3ኛ/ሰበር ችሎቱ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

**መ/ዐ**

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሠ/መ/ቁጥር 247351

ጥቅምት 05 ቀን 2017ዓ/ም

**ዳኞች ፡-  ብርሃኑ አመነው**

**በዕዉቀት በላይ**

**ቀነዓ ቂጣታ**

**ብርሃኑ መንግሥቱ**

**ማርታ ተካ**

**አመልካች፡-  አቶ ተመስገን መኮንን - አልቀረቡም**

**ተጠሪ ፡-  የኦሮሚያ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ - ዐ/ህግ ሞሮዳ ጉሉማ ቀረቡ**

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በጦር መሣሪያ ቁጥጥር እና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀፅ 4/1 እና 22/3 እና በወንጀል ሕግ አንቀፅ 418(1/ሀ) ስር የተደነገገዉን አተገባበር የሚመለከት ነው፡፡ክርክሩ የተጀመረው በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረበው ክስ ሲሆን የቀረበውም ክስ አጭር ይዘት - አመልካች የጦር መሣሪያ ቁጥጥር እና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀፅ 4/1 እና 22/3ን በመተላለፍ በነቀምቴ ከተማ ቀበሌ 03 የጨለለቂ መካነ ኢየሱስ ቤተ-ክርስቲያን በሚባል አካባቢ በቀን 28/01/2015 ዓ/ም ከቀኑ 6:00 አካባቢ በፀጥታ አካላት በተደረገ ብርበራ አንድ ባለ ሰደፍ ክላሽ የመለያ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ቁጥሩ TN9199/B68094 የሆነ ከተቆረጠ አንድ ካርታ ጋር፣ሪታይፋለኮን ሽጉጥ የመለያ ቁጥሩ RFLA/ 190308109 ከካርታው ጋር፣ ሪታይፋለኮን ሽጉጥ የመለያ ቁጥሩ RFLA/190321308 ከካርው ጋር፣ 3 ቤልጅግ ሽጉጥ የመለያ ቁጥር የሌለው፣ ሰባራ የሆነ የቱርክ ሽጉጥ የመለያ ቁጥሩ EP171042/54 ከካርታው ጋር፣3 ቤልጅግ ሽጉጥ የመለያ ቁጥሩ 601805 ከካርታው ጋር፣ አስር የካሪቫይን ጥይት እና እስታር ሽጉጥ የመለያ ቁጥሩ HN841993 የሆነ የስር 2ኛ ተከሳሽ ፍቃድ አውጥቶበት ያለው ከመኖሪያ ቤቱ ውስጥ ተገኝቷል የሚል ክስ መስርቶበታል፡፡

የክስ ማመልከቻዉ ለአመልካች እንዲደርሰዉ ተደርጎ ተነቦለት በሰጠዉ ቃል አርሶ አደር ሁኜ ቤቴ እና የሰብል ማሳዬ ስለተቃጠለብኝ የምተዳደረበት አጥቼ ይህንን መሣሪያ ለመነገድ ወይም ትርፍ ገንዘብ ለማግኘት ገዝቼ ለመሸጥ ብዬ እጄ ላይ ተያዘብኝ እንጂ ለማከማቸት አስቤ አይደለም፡፡እንደ አቃቤ ሕግ ክስ ጥፋት አልፈጸምኩም በማለት ክዶ ተከራክሯል፡፡ በመቀጠል ሁለት የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች ቀርበው የተሰሙ ሲሆን ምስክሮቹ በሰጡት ቃል - በቀን 28/01/2015ዓ/ም ከጧቱ 4:00 ላይ አዛዦችን የአመልካችን ቤት እንድንበረብር ትዕዛዝ ሰጥቶን ነቀምቴ ከተማ 03 ቀበሌ ሄደን አመልካችን ቤት በርብረን ስድስት ሽጉጥ አንድ ክላሽ አስራ አራት ጥይት አግኝተን ከአመልካች ጋር ይዘን ፖሊስ ጣቢያ ወስደነዋል፡፡አመልካች አንድ ሽጉጥ ሰው ነው እኔ ጋር ያስቀመጠው ብሎ ነበር፡፡ማን እንደሆነ አልነገረንም፡፡በሌላ በኩል የዐቃቤ ሕግ 1ኛ ምስክር አመልካች እነዚህን የጦር መሣሪያ ነግጄ እተዳደርበታለሁ ብሎ አመልካች ሲናገር እንደሰማ ሲያስረዱ 2ኛ ምስክር ደግሞ እነግዳለሁ ብሎ ሲናገር አልሰማሁም በማለት መስክረዋል፡፡ ይህንን ተከትሎ ዐቃቤ ሕግ በክሱ መሰረት አስረድቷል በማለት ፍርድ ቤቱ አመልካች ክሱን እንዲከላከል አዝዟል፡፡

በመቀጠል አመልካች አቅርቦ ባሰማቸዉ ሁለት መከላከያ ምስክሮቹ - አመልካች በፊት የእርሻ ሥራ የነበረው እና አርሶ አደር ሲሆን የእርሻ ሥራው ስለተቋረጠበት ልጆቹን የሚያስተዳድርበትን እና የሚያስተምርበትን ለማግኘት ብሎ እነዚህን የጦር መሣሪያ ጠግኖ ይሸጣል፡፡ለሚ ታደሰ ለሚባል ሰው ሊሸጥለት ተስማምተው በነጋታው ለሚ ፖሊስ አምጥቶ አስያዘው፡፡አመልካች መሣሪያውን ከየት እንዳመጣው አላውቅም፡፡ የንግድ ፍቃድ የለውም ሲሉ መስክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 58936 ላይ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃዎችን መርምሮ በቀን 17/05/2015 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ አመልካች ያቀረባቸው መከላከያ ምስክሮች አመልካች መሣሪያዎቹን ገዝቶ የሚሸጥ መሆኑን በማረጋገጥ ስላልመሰከሩለት አልተከላከሉለትም በማለት አመልካች በተከሰሱበት አዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀጽ 22/3 ስር ጥፋተኛ ነዉ ሲል ፍርድ ሰጥቷል፡፡በመቀጠል የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት መርምሮ ባስተላለፈዉ የቅጣት ዉሳኔ አመልካች በ5 ዓመት ከ6 ወር ፅኑ አስራት እና በብር 10,000.00 (አስር ሺሕ ብር) የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ወስኖበታል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 425224 ላይ በቀን 30/05/2015ዓ/ም በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 195/1 መሰረት በሰጠዉ ትእዛዝ ተጠሪን ሳያስቀርብ ሠርዞበታል፡፡ በመቀጠልም አመልካች የሰበር አቤቱታዉን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ቢሆንም ችሎቱ በመ/ቁጥር 422150 ላይ በቀን 24/06/ 2015 ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ የተፈጸመ ስህተት የለም በማለት ሠርዞበታል፡፡

አመልካች በቀን 11/08/2015ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉ ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታዉ አጭር ይዘት፡- አመልካች የእምነት ክህደት ቃሌን ስሰጥ ለክሱ ምክንያት የሆነው የጦር መሣሪያ በመኖሪያ ቤቴ ውስጥ መያዙን ሳልክድ ነገር ግን መሣሪያው ቤቴ ውስጥ ሊያዝ የቻለው መሣሪያውን በማከማቸት ዓላማ ሳይሆን መሣሪያ ለመነገድ ዓላማ መሆኑን ገልጬ ነበር፡፡የዐቃቤ ሕግ ምስክሮችም በወቅቱ መሣሪያውን ለንግድ ዓላማ እንደያዘ ነግሮን ነበር ብለዋል፡፡ያቀረብኳቸው የመከላከያ ምስክሮችም እነዚህን መሣሪያዎች ለመነገድ ዓላማ እንደያዝኳቸውና 1ኛው የዐቃቤ ሕግ ምስክር በመጀመሪያ ቀን ማስረጃዎቹን ለመግዛት ተነጋግሮ በሁለተኛው ቀን ፖሊሶችን ይዞ መጥቶ እንዳስያዘኝ ተናግሯል፡፡ በመሆኑም መሣሪያዎቹ በእጄ የተገኙት በመነገድ ዓላማ ስለመሆኑ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡በአዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀፅ 22/1 በጦር መሣሪያ መነገድ ወንጀል በሚመለከት የወንጀል ሕግ አንቀፅ 481 የተጠበቀ ስለመሆኑ በግልጽ ይደነግጋል፡፡ከዚህ የሕግ ድንጋጌ መረዳት እንደሚቻለው አንድ ሰው የጦር መሣሪያ ያለ ሕጋዊ ፍቃድ ይዞ ቢገኝ የሚጠየቅበት የሕግ ድንጋጌ በአዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀፅ 22/3 ስር ሳይሆን በወንጀል ሕግ አንቀፅ 481 ስር መሆን የሚገባው እንደሆነ ነው፡፡ስለሆነም በዚህ ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ ተብዬ ተመጣጣኝ የሆነ ቅጣት ሊወሰንብኝ ሲገባ ከተፈፀመው ድርጊት ጋር አግባብነት በሌለው በአዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀፅ 22/3 ስር የጥፋኝነት ውሳኔ መስጠቱ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ነው ተብሎ ይታረምልን በማለት አመልክቷል፡፡

ችሎቱ በአዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀፅ 22/1 ስር በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 481 ስር በጦር መሣሪያ ስለመነገድ የሚደነግገው ድንጋጌ እንዳልተሸረ ተደንግጓል፡፡በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 481(1/ሀ) ስር በሕጉ አንቀፅ 256 ስር ከተደነገገው አግባብ ውጪ ፈቃድ ሳይኖረው ወይም ሕግን ተቃራኒ በሆነ መንገድ ማናቸውም አይነት የጦር መሣሪያዎች ፈንጆች ወይም ጥይቶች በመነገድ ዓላማ የገዛ ያስቀመጠ ለሽያጭ ያቀረበ እንደሆነ በድንጋጌው ላይ በተመለከተው መሰረት እንደሚቀጣ ደንግጓል፡፡አዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀፅ 4/1 እና 22/3 እና በወንጀል ህግ አንቀጽ 418/1/ሀ ተደንግጓል፡፡ በድንጋጌዎቹ የተጠቀሱትን የጦር መሣሪያዎች መግዛት መሸጥ የወንጀል ተጠያቂነትን አስከትሎ የሚያስቀጣበትን አግባብ እና የሁለቱን ድንጋጌዎች ተግባራዊ አፈፃፀም ለመለየት እንዲሁም አመልካች ጥፋተኛ ተብሎ ሊቀጣ የሚገባው በየትኛው ድንጋጌ ነው የሚለውን ተጠሪ ባለበት እንዲመረመር ተጠሪ መልሱን እንዲሰጥ አዝዟል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ተጠሪ በቀን 22/12/2015ዓ/ም በተጻፈ መልሱ - አመልካች በክሱ ውስጥ የተጠቀሱ የጦር መሣሪያዎችን በሕግ ፊት የፀና ፍቃድ ሳይኖረው አከማችቶ የተገኘ መሆኑን አቃቤ ሕግ በማስረጃ አረጋግጧል፡፡አመልካች በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 35 መሰረት ስለ ወንጀሉ አፈፃፀም ቃል ሲሰጥ የተጠቀሰውን ብዛት ያለው የጦር መሣሪያ በቤቱ ውስጥ መገኘቱን አምኗል፡፡የቀረቡት የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎች በአመልካች ቤት የተገኘው የጦር መሣሪያዎች አመልካች በሕግ ፊት የፀና ፍቃድ ሳይኖው አከማችቶ የተገኘ መሆኑን እንጂ ለንግድ አላማ የጦር መሳርያ እንዳልያዘ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች አመልካችን በአዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀጽ 23/3 ስር ጥፋተኛ ነዉ በማለት ቅጣት በመወሰናቸዉ የተፈጸመ ስህተት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካችም የመልስ መልሱን በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

ከላይ አጠር ባለ መልኩ የተገለጸዉ በክልሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ውሳኔዎች እና የግራ ቀኙን ክርክር የሚመለከት ሲሆን እኛም ከፍ ሲል የተያዙትን ጭብጦች መሠረት በማድረግ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የሕግ ስህተት መፈጸም አለመፈጸሙን እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደተመረመረዉም በክሱ የተጠቀሱትን የጦር መሣሪያዎች አመልካች በቤቱ ዉስጥ ይዞ የነበረ መሆኑ በአመልካች የታመነና በማስረጃም የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ግራ ቀኙን ያከራከረዉ እና የዚህን ችሎት ዉሳኔ የሚሹ ነጥቦች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 481 እና የአዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀጽ 23/3 አንድነትና ልዩነት ምንድን ናቸዉ? የእነዚህ ድንጋጌዎች ተግባራዊ አፈጻጸም ምንድን ነዉ? እንዲሁም አመልካች በፈጸመዉ ድርጊት ጥፋተኛ ሊባል የሚገባዉ በየትኛዉ ድንጋጌ ነዉ? የሚሉ ናቸዉ፡፡

በመጀመሪያም በወንጀል ሕግ አንቀጽ 481 እና በአዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀጽ 23/3 አንድነትና ልዩነት ምንድን ናቸዉ? እንዲሁም የእነዚህ ድንጋጌዎች ተግባራዊ አፈጻጸም ምንድን ነዉ? የሚለዉን ጭብጥ መርምረናል፡፡ ይህንን ነጥብ የክርክር ጭብጥ ማድረግ ያስፈለገዉ ከጦር መሣሪያ ጋር የተያያዙ ድርጊቶችን ወንጀል አድርገዉ የሚደነግጉ ሁለት ሕግጋት በመኖራቸዉ ምክንያት ነዉ፡፡የመጀመሪያዉ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 481 ስር ስለጦር መሣሪያ መነገድ የተደነገገዉ ሲሆን ከተያዘዉ ጉዳይ ጋር የተያያዘዉ ንዑስ አንቀጽ ይዘት የሚከተለዉ ነዉ፡፡

<u>አንቀጽ 481 በጦር መሣሪያ መነገድ</u>

ንዑስ አንቀጽ (1/ሀ) — "*ማንም ሰዉ መንግሥትን አደጋ ላይ ስለመጣል በወንጀል ሕግ አንቀጽ 256 ስር ከተደነገገዉ አግባብ ዉጭ ፡- ሀ/ ፈቃድ ሳይኖረዉ ወይም ሕግን ተቃራኒ በሆነ መንገድ ማናቸዉንም አይነት የጦር መሣሪያዎች፣ፈንጂዎች፣ወይም ጥይቶች በመነገድ ዓላማ የሠራ፣ከዉጭ አገር ያስመጣ፣ወደ ዉጭ አገር የላከ፣ ያጓጓዘ፣ የገዛ፣ የተቀበለ፣ ያስቀመጠ፣ ያከማቸ፣የደበቀ፣ለሽያጭ ያቀረበ ወይም እንዲዘዋወር ያደረገ ወይም ያከፋፈል እንደሆነ ፤...የተባሉት ዕቃዎች መወረሳቸዉ ሳይቀር በመቀጮና ከአምስት*

ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ወይም ሁኔታዉ ከባድ በሆነ ጊዜ ከአስር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል " የሚል ነዉ፡፡

በዚህ ድንጋጌ መሠረት ፈቃድ ሳይኖር ወይም ሕግን ተቃራኒ በሆነ መንገድ በመነገድ ዓላማ ማናቸዉንም አይነት የጦር መሣሪያዎች፣ፈንጂዎች ወይም ጥይቶች የሠራ፣ከዉጭ አገር ያስመጣ፣ወደ ዉጭ አገር የላከ...ያስቀመጠ፣ ያከማቸ፣የደበቀ፣ለሽያጭ ያቀረበ... እና በደንጋጌዉ የተጠቀሱትን ሌሎች ተግባራትን መፈጸሙ የተረጋገጠበት ሰዉ በድንጋጌዉ የተመለከተዉ ቅጣት ይፈጸምበታል፡፡ስለሆነም ማንኛዉም ሰዉ ፈቃድ ሳይኖረዉ ወይም ሕግን ተቃራኒ በሆነ አኳኋን በመነገድ ዓላማ ማናቸዉንም አይነት የጦር መሣሪያ በቤቱ ወይም በይዞታዉ ስር በማድረግ ያስቀመጠ፣ያከማቸ ወይም ለሽያጭ ያቀረበ እንደሆነ ሊከሰስና ድርጊቱን መፈጸሙ ሲረጋገጥበት ጥፋተኛ ተብሎ ሊቀጣ የሚችለዉ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 481 መሠረት ይሆናል ማለት ነዉ፡፡

በሌላ በኩል የጦር መሣሪያ አስተዳደር ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀጽ 4 እና 22 ስር ከጦር መሣሪያና አጠቃቀም ጋር የተከለከሉና በወንጀል የሚያስጠይቁ ድርጊቶች ተደንግገዋል፡፡ በአመልካች ላይ በተመሰረተዉ የወንጀል ክስ ላይ የተጠቀሱት እና ተያያዥ ድንጋጌዎች በሚከተለዉ መሠረት የተደነገጉ ናቸዉ፡፡

የአዋጅ ቁጥር 1177/2012 <u>አንቀጽ 4 የተከለከሉ ተግባራት</u>

> ንዑስ አንቀጽ 4/1 - " በዚህ አዋጅ መሠረት ከተፈቀደዉ ሰዉ ዉጭ ማንኛዉም ሰዉ - የፀና ፈቃድ ሳይኖረዉ የጦር መሣሪያ ፣የጦር ሜዳ መነጽር፣በጦር መሣሪያ ላይ ሊገጠም የሚችል ማንኛዉንም አይነት መነጽር ወይም የጦር መሣሪያ ሲተኮስ ድምጽ ለማስወገድ የሚያገለግል መሣሪያ ወደ ሀገር ማስገባት፣ከሀገር ማስወጣት፣ መያዝ፣ ማስቀመጥ፣ ማከማቸት፣ መገልገል፣ ማሳየት፣ መደለል፣ መሸጥ፣ መግዛት፣ ማስተላለፍ፣ ማዘዋወር፣ ማጓጓዝ፣ ማምረት፣ ማሰልጠን፣ መጠገን ወይም ማስወገድ የተከለከለ ነዉ፡፡"

የአዋጁ <u>አንቀጽ 22 የወንጀል ተጠያቂነት</u>

ንዑስ አንቀጽ 1) "በጦር መሣሪያ መነገድ ወንጀል በሚመለከት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 481 የተጠበቀ ነዉ፡፡"

ንዑስ አንቀጽ 2) "ማንኛዉም ሰዉ በዚህ አዋጅ የተመለከተዉን ክልከላ እና ግዴታ በመተላለፍ የጸና ፈቃድ ሳይኖረዉ የጦር መሣሪያ፣የጦር ሜዳ መነጽር፣በጦር መሣሪያ ላይ ሊገጠም የሚችል ማንኛዉም አይነት መነጽር ወይም የጦር መሣሪያ ሲተኮስ ድምጽ ለማስወገድ

<u>ማስታወሻ</u>፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የሚያገለግል መሣሪያ ወደ ሀገር ያስገባ፣ከሀገር ያስወጣ፣ያስቀመጠ፣ የተገለገለ፣ ያሳየ፣ የደለለ፣ የሸጠ፣ የገዛ፣ ያጓጓዘ፣ያመረተ፣ያሰለጠነ፣የጠገነ ወይም ያስወገደ፣በማናቸዉም መንገድ ያስተላለፈ ወይም የያዘ እንደሆነ ከአንድ ዓመት እስከ ሶስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት እና ከአምስት ሺህ እስከ አስር ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡”

ንዑስ አንቀጽ 3) “በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተፈጸመዉ ወንጀል ብዛት ባለዉ የጦር መሣሪያ ሲሆን ቅጣቱ ከስምንት ዓመት እስከ ሃያ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከመቶ ሺህ እስከ ሁለት መቶ ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡”

በአዋጅ ቁጥር 1177/2012 መግቢያ ላይ ይህ አዋጅ ከወጣበት ዓላማዎች ዉስጥ አንዱ በሥራ ላይ ባሉ ሕጎችና አሠራሮች ያልተሸፈኑ ጉዳዮችን በዝርዝር ሕግ መደንገግ እና ወጥነት ያለዉን ሥርዓት መፍጠር እንደሆነ ተመልክቷል፡፡በዚህ መሠረት አስቀድሞ በወንጀል ሕግ ከተሸፈኑ ወንጀሎች መካከል አንዱ ከላይ ይዘቱ የተገለጸዉና በጦር መሣሪያ ስለመነገድ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 481 የተደነገገዉ ነዉ፡፡በአዋጁ አንቀጽ 22/1 ስር በግልጽ እንደተመለከተዉ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 481 የተደነገገዉ በዚህ አዋጅ አልተሻረም፤ ወይም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 22 እንዲተካ አልተደረገም፡፡ይልቁንም ሕግ አዉጪዉ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 481 ጸንቶ እንዲቀጥል እና አዋጁ በጦር መሣሪያ ከመነገድ ዉጭ የሆኑ ድርጊቶችን ብቻ የወንጀል ተጠያቂነትን እንዲያስከትል መደንገጉን በአዋጁ አንቀጽ 22/1 ስር በግልጽ አቋሙን ገልጿል፡፡

በመሆኑም ማንኛዉም ሰዉ የጸና ፈቃድ ሳይኖረዉ ወይም ሕግን ተቃራኒ በሆነ መንገድ ማንኛዉንም የጦር *መሣሪያ ከንግድ ሥራ ዓላማ እና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 256 ስር ከተደነገገዉ ማዕቀፍ ዉጭ በሆነ በሌላ* ሀሳብ ወይም ዓላማ ወደ ሀገር ዉስጥ ያስገባ፣ከሀገር ያስወጣ፣ የያዘ፣ ያስቀመጠ፣ የተቀበለ፣ ያከማቸ፣ የተገለገለ፣ ያሳየ፣ *የደበቀ፣ለሽያጭ ያቀረበ* ፣ የደለለ፣ የሸጠ፣ የገዛ፣ ያስተላለፈ፣ *ያከፋፈለ፣* ያዘዋወረ፣ ያጓጓዘ፣ የሠራ ወይም ያመረተ፣ ያሰለጠነ፣ የጠገነ ወይም ያስወገደ *እንደሆነ ጥፋተኛ ሆኖ ሊቀጣ የሚገባዉ በአዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀጽ 22 ስር በተመለከቱት አግባብነት ባላቸዉ ንዑሳን ድንጋጌዎች መሠረት ይሆናል፡፡*

ከእነዚህ ድንጋጌዎች አፈጻጸም ጋር በተያያዘ ሌላዉ ግልጽ መሆን ያለበት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 481(1/ሀ) ስር “በመነገድ ዓላማ” በሚል የተገለጸዉ ሀረግ እንዴት መታየት አለበት የሚለዉ ነዉ፡፡በዚህ ድንጋጌ መሠረት ተጠያቂ ለመሆን በመነገድ ዓላማ በድንጋጌዉ ላይ የተጠቀሱት ተግባራት መፈጸም ያለባቸዉ *የጸና የንግድ ፈቃድ ሳይኖር ወይም ሕግን ተቃራኒ* በሆነ አግባብ ሊሆን ይገባል፡፡ የንግድ ፈቃድ ሳይኖረዉ ወይም ሕግን ተቃራኒ በሆነ አግባብ *ለመነገድ ዓላማ* በድንጋጌዉ የተመለከተዉን ግዙፋዊ ፍሬ ነገር ተፈጽሟል ሊባል የሚቻለዉ ደግሞ *ማንኛዉም ሰዉ ጥቅም ለማግኘት ወይም ትርፍ ለማግኘት ብሎ የሞያ ሥራዉ*

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

*አድርጎ የጦር መሣሪያ የመሸጥ፣የመግዛት፣የመለወጥ ፣ የማስተላለፍ፣ለሽያጭ የማቅረብ ተግባር ሲፈጸም እና ለዚሁ ተግባር የጦር መሣሪያ የመጠገን፣ የማስቀመጥ እና የማከማቸት ተግባር ሲፈጸም ነዉ፡፡* ከዚህ አግባብ ዉጭ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 481(1/ለ) ስር የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛዉም ሰዉ የመነገድ ዓላማ ሳይኖረዉ ያለፈቃድ ወይም ሕግን ተቃራኒ በሆነ አግባብ በእጁ የሚገኘዉን ማንኛዉንም የጦር መሣሪያ የሸጠ፣ለሽያጭ ያቀረበ፣ ያስቀመጠ፣ያከማቸ፣የጠገነ እና ሌሎች በአዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀጽ 4 ስር የተከለከሉ ተግባራትን የፈጸመ እንደሆነ ተጠያቂ ሊሆን የሚገባዉ ከላይ እንደተገለጸዉ *በአዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀጽ 22 ስር በተመለከቱት አግባብነት ባላቸዉ ንዑሳን ድንጋጌዎች መሠረት ይሆናል፡፡*

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች በክሱ የተጠቀሱትን የጦር መሣሪያዎች በቤቱ ያስቀመጠዉ ወይም ያከማቸዉ ፈቃድ ሳይኖረዉ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡አመልካች ይህንን ድርጊት የፈጸመዉ በአርሶ አደርነት ሲተዳደር ቤቱ እና የሰብል ማሳዉ ስለተቃጠለበት የሚተዳደርበትን በማጣጡ የጦር መሣሪያ በመነገድ ትርፍ ገንዘብ ለማግኘት በማሰብ ገዝቶ ለመሸጥ በማሰብ እንደሆነ በመግለጽ በክሱ ላይ የተገለጸዉን ወንጀል ለመፈጸም አስቦ እንዳላከማቸ በመግለጽ ክዶ ተከራክሯል፡፡ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች የሰጡት ምስክርነት ቃል የሚያሳየዉ በክሱ የተጠቀሱት የጦር መሣሪያዎች በአመልካች ቤት ዉስጥ ተቀምጠዉ መገኘታቸዉን ሲሆን ይህም በአመልካች የተካደ አይደለም፡፡ይልቁንም የዐቃቤ ሕግ አንድ ምስክር አመልካች መሣሪያዎቹን በቤቱ ያስቀመጠዉ ለመነገድ ዓላማ እንደሆነ ከአመልካቹ መስማቱን መመስከሩ እና አመልካች ክሱን እንዲከላከል ከታዘዘ በኋላ አቅርቦ ባሰማቸዉ ምስክሮች አመልካች በፊት የእርሻ ሥራ የነበረው እና አርሶ አደር ሲሆን የእርሻ ሥራው ስለተቋረጠበት ልጆቹን የሚያስተዳድርበትን እና የሚያስተምርበትን ለማግኘት ብሎ እነዚህን የጦር መሣሪያ ጠግኖ እንደሚሸጥ ፤ለሚ ታደሰ ለሚባል ሰው ሊሸጥለት ተስማምተው በነጋታው ይህ ለሚ የተባለዉ ሰዉ ለፖሊስ ጠቁሞ እንደአስያዘዉ መስክረዋል፡፡ ይህ ምስክርነት ቃል በድምሩ ሲታይ አመልካች በቋምነት የሚተዳደርበትን የአርሶ አደርነት ሥራዉን በመተዉ ፈቃድ ሳይኖረዉ ወይም ለሕግ ተቃራኒ በሆነ አግባብ ጥቅም ወይም ትርፍ ለማግኘት በማሰብ ተጠቃሾቹን የጦር መሣሪያዎች እየገዛ እና እየጠገነ ለሽያጭ የማቅረብ ተግባር ወስጥ መግባቱን የሚያሳይ ነዉ፡፡በመሆኑም አመልካች የተከሰሰበትን ድርጊት የፈጸመዉ የሙያ ሥራዉ አድርጎ በተጠቀሱት የጦር መሣሪያዎች የመነገድ ድርጊት መፈጸሙን የሚያሳይ ነዉ፡፡

በመሰረቱ በአገራችን የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሥርዓት መሰረት ሕገ-ወጥነቱና አስቀጪነቱ በሕግ የተደነገገዉን በማድረግ የሚፈጸም የወንጀል ድርጊት ወይም አል ድርጊት ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮችን በአንድነት በሚያሟላ አኳኋን መፈጸሙ በፍርድ ቤት የተረጋገጠበት ወንጀል ፈጻሚ በወንጀል ሕጉ እና አግባብነት ባለዉ ሌላ ሕግ የተደነገገዉን ቅጣት መቀጣት ይገባዋል፡፡ አንድ ሰው በወንጀል ደርጊት ተጠያቂ የሚሆነው የተከሰሰበትን ድርጊት ወንጀል አድርጎ በሚደነግገዉ ሕግ ላይ በተመለከተዉ መሠረት ድርጊቱን ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት መፈጸሙ በማስረጃ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ

አንቀጽ 58 እና 59 ስር ተደንግጓል፡፡ በዚህ መልኩ ተከሳሹ ጥፋተኛ ሆኖ ሊቀጣ የሚችለዉ በወንጀል ሕጉ ልዩ ድንጋጌዎችና በሌላ ልዩ ሕግ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል ስለመፈጸሙ ዐቃቤ ሕግ ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮችን በሚያሳይ አኳኋን በማስረጃ ሲያስረዳ ነዉ(የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23 ይመለከቷል)፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን እና በይግባኝ ሰሚነት የሚዳኙ ፍርድ ቤቶች የማስረጃ አቀራረብን፣ አግባብነትን፣ ተቀባይነትን እና ማስረጃ አቅርቦ አንድን ፍሬ ነገር የማስረዳት ሸክም የሚመለከቱ መርሆዎች (Principles of Production, relevancy, admissibility and burden of proof of evidence) አተገባበር በሚቃረን አኳኋን እንዲሁም የማስረጃ ምዘናን ወይም የማስረዳት ደረጃን (standards of proof or weight of evidence) የሚመለከቱ መሰረታዊ መርሆዎች በመጣስ የመጨረሻ ዉሳኔ መስጠታቸዉ በግልጽ ሲረጋገጥ፤ በተጨማሪም በአንድ ማስረጃ ይዘት ላይ በግልጽ የተመለከተዉን ወይም በምስክሮች ተመስክሮ የተረጋገጠዉን ፍሬ ነገር በአግባቡ ያላገናዘበ ዉሳኔ ሲሰጡ እና ዉሳኔ የሚሻዉ የፍሬ ነገር ጭብጥ መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ አስፈላጊ ለሆነ ማስረጃ ተገቢዉን ዋጋ ሳይሰጡ ዉሳኔ መስጠት እንዲሁም በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠዉን ነጥብ ከሕጉ ጋር ሳያገናዝቡ መወሰን ማስረጃ ወደ መመዘን ዉስጥ ተገብቷል የሚያስብል ሳይሆን እንደመሰረታዊ የሕግ ስህተት ተቆጥሮ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚገባ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በሰ/መ/ቁጥር 45595፣64813(ቅጽ 12)፣ 225975 ፣228017 (ያልታተሙ) እና በሌሎች መዛግብት ላይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

በያዝነዉ ጉዳይ ከላይ በዝርዝር እንደተገለጸዉ አመልካች በክሱ የተጠቀሰዉን ድርጊት የእምነት ክህደት ቃሉን በሠጠበት አግባብ ለመነገድ ዓላማ ሲል እንደፈፈጸመ ባቀረባቸዉ መከላከያ ምስክሮች ከማስረዳቱም በተጨማሪ የዐቃቤ ሕግ አንደኛዉ ምስክርም ይህንኑ በሚያጠናክር አኳኋን መስክረዋል፡፡በአመልካች ስለመፈጸሙ በማስረጃ የተረጋገጠዉ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ(የሀሳብ ክፍል) ፍሬ ነገሮች የሚያሳዩት አመልካች በክሱ የተጠቀሰዉን ድርጊት የፈጸመዉ በጦር መሣሪያ ለመነገድ ዓላማ ሆኖ እያለ የሥር ፍርድ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ድርጊቱን የፈጸመዉ ለመነገድ ዓላማ ስለመሆኑ በማስተባበል አልተከላከለም የሚል ድምዳሜ ላይ መድረሱ በማስረጃ የተረጋገጠዉን የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 481(1/ሀ) ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮችን ያላገናዘበ በመሆኑ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23/2 የተደነገገዉን መርህ እና የማስረጃ ምዘና መሠረታዊ መርህ አተገባበር የሚቃረን እንደሆነ አረጋግጠናል፡፡

ሲጠቃለል የንግድ ፈቃድ ሳይኖረዉ ወይም ሕግን ተቃራኒ በሆነ አግባብ ማንኛዉም ሰዉ ጥቅም ለማግኘት ወይም ትርፍ ለማግኘት በማሰብ የሞያ ሥራዉ አድርጎ የጦር መሣሪያ የመሸጥ፣ የመግዛት፣ የመለወጥ ፣ የማስተላለፍ፣ለሽያጭ የማቅረብ ተግባር ሲፈጽም እና ለዚሁ ተግባር የጦር መሣሪያ የመጠገን፣ የማስቀመጥ እና የማከማቸት ተግባር መፈጸሙ ሲረጋገጥ ጥፋተኛ ሆኖ ሊቀጣ የሚገባዉ በጦር መሣሪያ ስለመነገድ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በወንጀል ሕግ አንቀጽ 481(1/ሀ) ስር በተደነገገዉ መሠረት ነዉ ብለናል፡፡ አንድ የወንጀል ደርጊት በሕዝቡና በመንግሥት ላይ የሚያደርሰዉን ጉዳት መጠን በማመዛዘን ወንጀሉ የሚያስቀጣዉን ቅጣት በሕግ መደንገግ ሕግ አዉጪ የሆነዉ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነዉ፡፡የፍርድ ቤት ተግባርና ኃላፊነት ተከሳሹ ጥፋተኛ በተባለበት የሕግ ድንጋጌ ላይ ንየተደነገገዉ ቅጣት መነሻ በማድረግ በወንጀል ሕጉና በቅጣት አወሳሰን መመሪያዉ ላይ የተደነገገዉን የቅጣት አወሳሰን መርሆዎችንና ደንቦችን በመከተል የቅጣት ዉሳኔ ማስተላለፍ ነዉ፡፡ አመልካች በቋምነት የሚተዳደርበትን የአርሶ አደርነት ሥራዉን በመተዉ ፈቃድ ሳይኖረዉ ወይም ለሕግ ተቃራኒ በሆነ አግባብ ጥቅም ወይም ትርፍ ለማግኘት በማሰብ ተጠቃሾቹን የጦር መሣሪያዎች እየገዛ እና እየጠገነ ለሽያጭ የማቅረብ ተግባር ወስጥ መግባቱን ስለተረጋገጠ የፈጸመዉ ድርጊት የሙያ ሥራዉ አድርጎ በተጠቀሱት የጦር መሣሪያዎች የመነገድ ድርጊት መፈጸሙን የሚያሳይ ነዉ፡፡ በመሆኑም የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካችን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 481(1/ሀ) ስር ጥፋተኛ ነዉ ብሎ ቅጣት መወሰን ሲገባዉ በአዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀጽ 22/3 ስር ጥፋተኛ ነዉ በማለት ቅጣት መወሰኑ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሸ) እና 10(1/ሐ) መሠረት ሊታረም የሚገባዉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ እንዲሁም ጉዳዩን በይግባኝ እና በሰበር የተመለከተዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስህተቱን ማረም ሲገባዉ ዉሳኔዉን በትእዛዝ ማጽናቱ ሊታረም የሚገባዉ ስህተት ነዉ ብለናል፡፡ በመሆኑም አመልካች እንደፈጸመ የተረጋገጠዉ የወንጀል ድርጊት በጦር መሣሪያ መነገድ ወንጀል በመሆኑ በክሱ የተጠቀሰዉን የአዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀፅ 4/1 እና 22/3 ድንጋጌ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 113/2 መሰረት ወደ ወንጀል ሕግ አንቀጽ 481(1/ሀ) በመለወጥ አመልካች በወንጀል ሕግ አንቅ 481(1/ሀ) ስር ጥፋተኝ ነዉ ሲል ችሎቱ ፍርድ ሰጥቷል፡፡

ቅጣትን በተመለከተም የወንጀል ቅጣትና የጥንቃቄ እርምጃዎች የሚወሰነዉ በወንጀል ሕጉ ታላቅ ክፍል ስለወንጀል ቅጣት አወሳሰን የተደነገጉ መርሆዎችንና ሁኔታዎችን እንዲሁም ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው የሚደነግጉትን የልዩ ክፍሉ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ መሆኑን፣ የወንጀል አድራጊውን ግላዊ የአደገኛነት መጠን፣ ያለፈ የህይወት ታሪኩን፣ ወንጀል ለማድረግ ያነሣሡትን ምክንያቶችና የአሣቡን ዓላማ፣ የግል ኑሮውን ሁኔታ፣ የትምህርቱን ደረጃ፣ እንዲሁም የወንጀሉን ከባድነትና የአፈፃፀሙን ሁኔታዎች በማመዛዘን መሆኑን፣ የወንጀል ሕግ ልዩ ክፍል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነዉ ፍርድ ቤቱ በሕጉ የተመለከቱትን የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶችን በመያዝ እጅግ ቀላል ከሆነው ቅጣት አንስቶ እስከ ከባዱ ድረስ ያለውን በጥንቃቄ በመመርመር ለእያንዳንዱ ጉዳይ ተገቢ የሆነውን ቅጣት እንደሚወስን በወንጀል ሕጉ እና በቅጣት አወሳሰን መመሪያዉ ላይ የተመለከተዉ የቅጣት አወሳሳን ደንብ ያሳያል (የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 82-88 ይመለከቷል)፡፡በዚህ መሠረት በአመልካች እጅ የተገኙትን የጦር መሣሪያዎች ብዛት ያላቸዉ መሆኑን ከግምት በማስገባት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 481(1/ሀ) ስር ከተደነገጉት አማራጭ ቅጣቶች መካከል ከአስር ዓመት ጽኑ እስራት የማይበልጥ የሚለዉን የቅጣት አማራጭ ይዘናል፡፡ በመቀጠል ወንጀሉ ደረጃ ያልወጣለት በመሆኑ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሠረት ለቅጣቱ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ደረጃ በማዉጣት ደረጃዉን መካከለኛ ደረጃ ላይ በመመደብ መነሻ ቅጣት 5 ዓመት ጽኑ እስራት ይዘናል፡፡ይህም በእርከን 20 ላይ የሚያርፍ ነዉ፡፡ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት የቅጣት ማክበጃ እንዳላቀረበ በመገለጹ የስር ፍርድ ቤት ለአመልካች የያዘለትን ሦስት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን በመያዝ ቅጣቱን ከእርከን 20 ወደ እርከን 17 ዝቅ በማድረግ ችሎቱ በእርከኑ የተመለከተዉን ፍቅድ ሥልጣን ከግምት በማስገባት አመልካችን ያርማል፤ መሰል ወንጀለኞችን ያስጠነቅቃል ብለን ባመንበት በ3 (ሦስት) ዓመት ከ11(አስራ አንድ )ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጣ በማሻሻል ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ዉሳኔ</u>

1. የምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 58936 ላይ በቀን 17/05/2015 ዓ/ም የሰጠዉ የጥፋተኝነት እና የቅጣት ዉሳኔ ፣የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የምዕራብ ቋሚ ችሎት በመ/ቁጥር 425224 ላይ በቀን 30/05/2015 ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ እና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 422150 ላይ በቀን 24/06/2015 ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 መሰረት ተሻሽለዋል፡፡
2. አመልካች በጦር መሣሪያ የመነገድ ወንጀል በመፈጸሙ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 481(1/ሀ) ስር ጥፋተኛ ነዉ ብለናል፡፡በዚህ መሠረት አመልካች ከዚህ ወንጀል ጋር በተያያዘ የታሰረበት ካለ የሚታሰብለት ሆኖ በ3 (በሦስት) ዓመት ከ11(አስራ አንድ )ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ተሻሽሎ ተወስኗል፡፡
3. ከአመልካች የተያዙ የጦር መሣሪያዎች እንዲወረሱ የተሰጠዉ ዉሳኔ አልተነካም፡፡

## <u>ትዕዛዝ</u>

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ እንዲያዉቁት ለክልሉ ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡እንዲሁም ማረሚያ ቤቱ በዚህ ዉሳኔ መሰረት እንዲያስፈጽም አመልካች ታስሮ ለሚገኝበት ማረሚያ ቤት የዉሳኔዉ ግልባጭ ይተላለፍ፡፡ ሲጠይቁ ግልባጩ ለግራ ቀኙም ይሰጣቸዉ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

*መ/ዐ*

<u>ማስታወሻ</u>፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁጥር---247512

ጥቅምት 06 ቀን 2017 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ብርሃኑ መንግስቱ

ማርታ ተካ

**አመልካች**:- ወ/ሮ አበጁ አስማማዉ -አልቀረቡም

**ተጠሪ**፡- ወ/ሮ ካሳዬ መክብብ -አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ቤትና ይዞታን የተመለከተ ጉዳይ ሲሆን የተጀመረው በደባርቅ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍ/ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 01-04531 የካቲት 17 ቀን 2015 ዓ.ም ተሰጥቶ በክልሉ ሰበር ችሎት በተሰጠ ትዕዛዝ የጸናዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በሚል ነዉ፡፡

**ማስታወሻ**፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት፡- በድብ-ባህር የገጠር ከተማ ዉስጥ በምስራቅ ጠጋዬ፤ በምዕራብ ጥርጊያ፤ በሰሜን ይሳቅ እና በደቡብ አስማረ የሚዋሰን ስፋቱ 40 ሜትር በ25 ሜትር የሆነዉን የእናታቸዉ በነበረ ቦታ ላይ አመልካች መብት ሳይኖራቸዉ የሳር ቤት ሰርተዉበት ልትለቅላቸዉ ስላልቻሉ አመልካች የሰሩትን ቤት አፍርሰዉ ቦታዉን እንዲለቁላቸዉ እንዲወሰን የሚጠይቅ ነዉ፡፡

አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስ፡- ቦታዉ የተጠሪ አይደለም፡፡ አመልካች ይዞታዉን ከያዙት 23 ዓመት ያልፈዋል፤ ስለሆነም ተጠሪ ሊጠይቋቸዉ እንደማይገባና ክሱ ዉድቅ ለደረግ እንደሚገባዉ በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡

የደባርቅ ወረዳ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ፣ ማስረጃዎችን ሰምቶና መርምሮ፡- አመልካች ክርክር ያስነሳዉን ይዞታ ያገኙት ባለቤታቸዉ የነበረዉ አቶ ንጉሴ መኩሪያዉ በ160 ብር ባዶ ቦታዉን ከአቶ የኑስ ታከለ ገዝቶ የሰጣቸዉ መሆኑን፤ የኑስ ታከለም የገዛዉ መሆኑን እንዲሁም የቦታዉ ሕጋዊ ባለይዞታ የተጠሪ ወላጅ እናት መሆናቸዉ ተጠሪ በምስክር ያስረዱ ሲሆን አመልካች በሕጋዊ መንገድ

የያዙ መሆናቸዉን ባለማስረዳታቸዉ፤ በይዞታዉ ላይ አመልካች ቤት የገነቡት ባለይዞታዉ ሳይቃወም ቢሆንም የገነቡትን ቤት በራሳቸዉ ወጭ አፍርሰዉ ቦታዉን ለቅቀዉ ለተጠሪ ያስረክቡ በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት የአሁን አመልካች ባቀረቡት ይግባኝ መነሻነት ጉዳዩን የተመለከተዉ የሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮና መርምሮ በወረዳዉ ፍ/ቤት ክስ ለመስማት ሰኔ 13 ቀን 2009 ዓ.ም በተያዘዉ ዕለት ግራ ቀኙ በሽምግልና ጉዳያቸዉን ለመጨረስ ከሄዱ በኃላ ክስ አንስቻለሁ የሚል አቤቱታ ባልቀረበበት ፍ/ቤቱ በራሱ ተነሳሽነት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 278(3) በመጥቀስ መዝገቡን የማንቀሳቀስ መብት ጠብቆ መዝጋቱን፤ መዝገቡ ከተዘጋ ከሦስት ዓመት በኃላ እንደገና በማንቀሳቀስ የሰጠዉ ዉሳኔ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ዓላማ የማያሳካ እና የተከራካሪ ወገኖችን የእኩልነት መብት በሚጥስ መልኩ የተሰጠ ዉሳኔ ነዉ በማለት የወረዳዉን ፍ/ቤት ዉሳኔ በአብላጫ ድመጽ በመሻር ወስኗል፡፡ ተጠሪ በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝተዉ ባቀረቡት ይግባኝ መነሻነት ጉዳዩን የተመለከተዉ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ደግሞ ግራ ቀኙን አከራክሮና መርምሮ የወረዳዉ ፍ/ቤት መዝገቡን በራሱ አነሳሽነት የማንቀሳቀስ መብት ጠብቆ ከዘጋ በኃላ መዝገቡን እንዲንቀሳቀስ በማድረግ አከራክሮ መወሰኑ የሥነ-ሥርዓት ግድፈት የተፈጸመበት ነዉ ተብሎ በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት መወሰኑ ስህተት ነዉ በማለት የከፍተኛዉን ፍ/ቤት ዉሳኔ በመሻር የወረዳዉን ፍ/ቤት ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝተዉ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወምና መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በሚል ነዉ፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘት፡- ክርክር ያስነሳዉን ቤትና ቦታ የገዙት ከተጠሪ እናት ሳይሆን ከአቶ የኑስ ታከለ መሆኑን ሻጭ ቀርቦ መስክሯል፡፡ አመልካች ቤት ሠርተዉበት ከ28 ዓመት በላይ የኖሩበት፤ የተጠሪ እናት ከሞቱ 20 ዓመት ከሞላዉ በኃላ የዉርስ ማስረጃ አዉጥተዉ ያቀረቡት ክስ በ10 ዓመት ይርጋ ይታገዳል በማለት ያቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በስር ፍ/ቤቶች መታለፉ ስህተት ነዉ፡፡ ከመሬት ኮሚቴዎች መካከል 3ቱ ይዞታዉ የአመልካች ነዉ ሲሉ 3ቱ ደግሞ አናዉቅም በማለት ፈርመዉ ባረጋገጡበት ሁኔታ የወረዳዉ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ካረጋገጠዉ በተቃራኒ የወረዳዉ ፍ/ቤት ይዞታዉ የተጠሪ መሆኑ ተረጋግጧል፤ ደብተርም አላት በማለት አመልካች ቤቱን አፍርሳ እንድትለቅ መወሰኑ ስህተት ነዉ፡፡ ባለመሬቶች ፈቅደዉ የሠሩት ቤት ባለቤት አመልካች መሆን ሲገባቸዉ የስር ፍ/ቤት የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1179 ድንጋጌን ያለአግባብ በመተርጎም አመልካች ቤቱን አፍርሰዉ እንዲነሱ መወሰኑ ስህተት ነዉ፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 278 መሠረት ተጠሪ ክስ እንዲዘጋላቸዉ ሳያመለክቱ ፍ/ቤቱ በራሱ ተነሳሽነት የመክሰስ መብት ጠብቆ መዝጋቱ መሠረታዊ የሕግ ጥሰት ያለበት ዉሳኔ ሆኖ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተሽሮ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ዉሳኔ እንዲጸናላቸዉ የሚጠይቅ ነዉ፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የወረዳዉን ፍ/ቤት ዉሳኔ የሻረዉ በፍሬ ጉዳይ ላይ የቀረበዉን ይግባኝ መርምሮ ሳይሆን የወረዳዉ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 278 መሠረት የተጠሪን ክስ ለጊዜዉ ዘግቶ የማንቀሳቀስ መብት ፍ/ቤቱ በራሱ ጠብቆ ከ3 ዓመት በኃላ አንቀሳቅሶ መወሰኑ ተገቢ አይደለም በሚል በሆነበት፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የዞኑን ከፍተኛ ፍ/ቤት ዉሳኔ ሲሽር በፍሬ ጉዳይ ይግባኙ ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ እንዲወስን ማድረግ ሲገባዉ ወይም ራሱ አካራክሮ መወሰን ሲገባዉ የአመልካችን የይግባኝ መብት ሊያጣብብ በሚችል መልኩ የወረዳዉን ፍ/ቤት ዉሳኔ ያጸናበትን አግባብነት ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341፣ 342 እና 343 ድንጋጌዎች እንዲሁም ይህ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 44545 ከሰጠዉ ገዥ ትርጉም አንጻር ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ በሰበር ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ ለሰበር አቤቱታዉ የሰጡት መልስ ይዘት በአጭሩ፡- ክርክር ያስነሳዉ ባዶ ቦታ የእ/ይ የርባለም ነበር፤ ለወ/ሮ አብነት እንዳለ ሸጠችዉ፤ ከዚያም ለአቶ የኑስ ታከለ ሸጠችለት፤ አቶ የኑስ ታከለ ደግሞ ለአመልካች ባል ለአቶ ንጉሴ መኩሪያ ሸጠ በማለት ያቀረበችዉ የሰበር አቤቱታ የሽያጭ ዉል ባልቀረበበትና ቀርቦም ቢሆን ባዶ ቦታ ስለማይሸጥ ተገቢነት የለዉም፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 278 የቀረበዉ መቃወሚያ በተመለከተ በክርክር ላይ እያለን ጉዳዩ ለሽምግልና ተመርቶ በሽምግልና ስምምነት የማያልቅ ከሆነ መዝገቡ እንደሚታይ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

ተደርጎ በሽማግሌ ቀጠሮ ብዛት ቆይተዉ አመልካች ባለመቅረባቸዉ በስምምነት ሊቋጭ ባለመቻሉ የተዘጋዉ መዝገብ ተንቀሳቀሰ እንጂ በተጠሪ አለመቅረብ ምክንያት መዝገቡ ተዘግቶ እንዲንቀሳቀስ ባለመደረጉ የተፈጸመ ስህተት የለም፡፡ የስር ፍ/ቤት ማስረጃዎችን ሰምቶና አጣርቶ ክስ የቀረበበት ቦታ የተጠሪ ወላጅ እና የወ/ሮ ሙሉ ሀይሌ የገመድ መሬት እንደሆነ አረጋግጦ የሰጠዉን ዉሳኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤቶች ማጽናታቸዉ ስህተት የሌለበት በመሆኑ የአመልካች አቤቱታ ዉድቅ እንዲደረግ በመጠየቅ ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም ሰኔ 06 ቀን 2016 ዓ.ም በተዘጋጀ 2 ገጽ የሰበር አቤቱታቸዉን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን እኛም አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡ የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር መርምረን እንደተረዳነዉ የወረዳዉ ፍ/ቤት ጉዳዩ በክርክር ሂደት ላይ ባለበት ሁኔታ ግራ ቀኙ ጉዳዩን በሽምግልና ለመጨረስ ጠይቀዉ ከሄዱ በኃላ ዉጤቱን ለመጠባበቅ በተሰጠዉ ቀጠሮ ግራ ቀኙ ባለመቅረባቸዉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 278 ድንጋጌን መሠረት በማድረግ የወረዳዉ ፍ/ቤት በራሱ ተነሳሽነት የተጠሪን ክሱን እንደገና የማንቀሳቀስ መብጥ ጠብቆ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ መዝገቡ ከተዘጋ ሦስት ዓመት በኃላ ተጠሪ ቀርበዉ በማመልከታቸዉ መዝገቡን በማንቀሳቀስ ግራ ቀኙን አከራክሮ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ዉሳኔ ሰጥቶበታል፡፡ እዚህ ላይ የወረዳዉ ፍ/ቤት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 278 ድንጋጌን መሠረት በማድረግ በራሱ ተነሳሽነት የተጠሪን መዝገቡን የማንቀሳቀስ መብት ጠብቆ መዝገቡን የመዝጋቱ ሥነ-ሥርዓታዊነት ሊያከራክር ቢችልም ፍ/ቤቱ በዚህ አግባብ መዝገቡን ሲዘጋዉ መዝገቡ በዚህ አግባብ ሊዘጋ እንደማይገባ በመግለጽ አመልካች በወቅቱ ስህተት ነዉ ያሉትን በይግባኝ ያሳረሙበት አግባብ ባለመኖሩ ተጠሪ መዝገቡን የማንቀሳቀስ መብታቸዉ ተጠብቆ የተዘጋዉን መዝገብ እንዲንቀሳቀስላቸዉ በማድረጋቸዉ መብታቸዉን የሚያጡበት አግባብ ባለመኖሩ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት መዝገቡ የተዘጋበትና የተንቀሳቀሰበት አግባብነት ላይ በመመስረት የሰጠዉን ዉሳኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መሻሩ የሚነቀፍ አይደለም፡፡

በሌላ በኩል የወረዳዉ ፍ/ቤት የዘጋዉን መዝገብ በማንቀሳቀስና ፍሬ ጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ ጭምር አመልካች የይግባኝ ቅሬታቸዉን ለዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ይግባኝ ሰሚዉ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የወረዳዉ ፍ/ቤት በራሱ ተነሳሽነት የዘጋዉን መዝገብ አንቀሳቅሶ መወሰኑ ተገቢ አይደለም በሚል የወረዳዉን ፍ/ቤት ዉሳኔ ሻረ እንጂ በፍሬ ጉዳዩ ላይ የቀረበዉን የአመልካች ቅሬታ መርምሮ ዉሳኔ አልሰጠበትም፡፡ እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የዞኑን ከፍተኛ ፍ/ቤት ዉሳኔ መሻሩ ተገቢ ቢሆንም አመልካች የወረዳዉ ፍ/ቤት በፍሬ ጉዳዩ ላይ የሰጠዉን ዉሳኔ በመቃወም ለዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበዉን የይግባኝ ቅሬታ አስመልክቶ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341 መሰረት የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተመልክቶት እንዲወስን ወይም ራሱ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት

ግራ ቀኙን አከራክሮበት ዉሳኔ ባልሰጠበት ሁኔታ በደፈናዉ የወረዳዉን ፍ/ቤት ዉሳኔ በማጽናት የሰጠዉ ዉሳኔ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 44545 የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341፣ 342፣ 343 እና ተከታዮችን ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ ይግባኝ ሰሚዉ ፍ/ቤት በዋናዉ ጉዳይ ላይ የራሱን ዉሳኔ ካላሳለፈና የበላይ ችሎቱ የይግባኝ ሰሚዉን ፍ/ቤት ዉሳኔ ካልተቀበለዉ በዋናዉ ጉዳይ ላይ ዉሳኔ ሊሰጥበት እንደሚገባ የሰጠዉን አስገዳጅ ትርጉም ያላገናዘበ፤ የአመልካችን የይግባኝ መብት ያጣበበ እና ሥነ-ሥርዓታዊ ባለመሆኑ በዚህ ረገድ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በደፈናዉ የወረደዉን ፍ/ቤት ዉሳኔ ማጽናቱ ተገቢ ባለመሆኑ ስህተቱ ሊታረም እና በፍሬ ጉዳዩ ላይ የቀረበዉን ቅሬታ መርምሮና አከራክሮ ዉሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩ ለዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ሊመለደስለት ይገባል፡፡

ሲጠቃለል የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ መሻሩ ተገቢ ቢሆንም አመልካች በፍሬ ጉዳዩ ዉሳኔ ላይ ያቀረበዉ ቅሬታ በይግባኝ ሰሚዉ ፍ/ቤት ዉሳኔ ባልተሰጠበት ሁኔታ የወረዳዉ ፍ/ቤት በፍሬ ጉዳዩ ላይ የሰጠዉን ዉሳኔ ማጽናቱ የአመልካችን የይግባኝ መብት ያጣበበና ሥነ-ሥርዓታዊ ባለመሆኑ፤ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 44545 የሰጠዉን አስገዳጅ ትርጉም ያላገናዘበ፤ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሸ) እና አንቀጽ 10(1/) ስር ከተደነገገዉ መመዘኛ አንጻር ሲታይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1. በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 01-04531 ቀን 2015 ዓ.ም ተሰጥቶ እና በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ. 03-122481 ግንቦት 08 ቀን 2015 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ የጸናዉ ዉሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1/ለ) መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ መሻሩ በአግባቡ ነዉ ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. አመልካች በወረዳዉ ፍ/ቤት በፍሬ ጉዳዩ ላይ በተሰጠዉ ዉሳኔ ላይ ያቀረቡት የይግባኝ ቅሬታ አስመልክቶ ይግባኝ ሰሚዉ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ዉሳኔ ባልሰጠበት ሁኔታ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ምንም ሳይል አልፎት የወረዳዉን ፍ/ቤት ዉሳኔ ማጽናቱ የአመልካችን የይግባኝ መብት ያጣበበ እና ሥነ-ሥርዓታዊ ባለመሆኑ በዚህ ረገድ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የወረዳዉን ፍ/ቤት ዉሳኔ በማጽናት የሰጠዉ የዉሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡

<u>ማስታወሻ</u>፡ - ይህ የሰበር ችሎት ዉሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

4. የሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የዘጋዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ አመልካች በፍሬ ጉዳዩ ላይ ያቀረበዉን የይግባኝ ቅሬታ አስመልክቶ ግራ ቀኙ ያደረጉትን ክርክር ተመልክቶ ወይም እንደገና አከራክሮ ተገቢዉን ይወስን ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343(1) እና በሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(2) መሰረት ጉዳዩን መልሰንለታል፡፡ ይጻፍ፡፡
5. ግራ ቀኙ በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

የሰ/መ/ቁጥር 247535
ጥቅምት 05 ቀን 2017 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው
በዕውቀት በላይ
ቀነዓ ቂጣታ
ብርሃኑ መንግስቱ
ማርታ ተካ

አመልካች፡- አቶ አፈንዲ መሐመድ አሊዪ ጠበቃ መታሰቢያ ኃይልዬ

ተጠሪ፡- የሐረር ክልል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ

**መዝገቡ መርምረን ተከታዩ ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ግንቦት 21 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ በሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 21652፤ አመልካች የግድያ ወንጀሉ እንዲፈፀም በማነሳሳት ወንጀል ተሳትፈሀል በማለት ሚያዝያ 11 ቀን 2014 ዓ.ም ጥፋተኛ በማለት፤ ሚያዝያ 17 ቀን 2014ዓ.ም የሰጠው የቅጣት ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ግራቀኙ ይግባኝ ያላባቸው በመ.ቁ 06073፤ 06098 እና 06104 መዝገቦች በማጣመር ህዳር 12 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ በማጽናት በመ.ቁ 00510፤ የካቲት 21 ቀን 2015ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ተጠሪ የአሁኑ አመልካች ስር 1ኛ ተከሳሽ፤ በዚህ መዝገብ የክርክሩ ተካፋይ ያልሆነ አብዱልሀፊዝ ሰቡር የተባለ የፖሊስ አባል 2ኛ ተከሳሽ በማድረግ በሐረሪ ክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ይዘት በአጭሩ፡- ተከሳሾች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32/1(ሀ) (ለ) ፤33፤36 እና 540 ድንጋጌን በመተላለፍ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተከፋይ በመሆን ጥር 26 ቀን 2013ዓ.ም ከጠዋቱ 5፡00 ሰኣት አካባቢ በሐረር ሕ/ክ/መንግስት ድሬ ጠያራ ወረዳ ሲጊቻ ቀ/ገ/ማህበር በልዩ ቦታው ድሬ ጠፌ እየተባለ በሚጠራው ስፍር የአሁኑ አመልካች) ስር 1ኛ ተከሳሽ ስር 2ኛ ተከሳሽ የነበረውን የፖሊስ አባል ሚች ከድር ዩንስ የተባለውን በጥይት መቶ እንዲገድለው በማንሳሳት ስር 2ኛ ተከሳሽም ሟች ከዲር ዮንስን በቀጥታ ደረቱ ላይ በመተኮስ በመግደሉ በፈጸሙት በተራ የሰው መግደል ወንጀል ተከሰዋል የሚል ሲሆን በተጨማሪም በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁ 113 መሰረት በወ/ህ/ቁ 541 መሰረት በአማራጭ ክስም ቀርበዋል፡፡

የአሁኑ አመልካች ክሱ ተነቦላቸው እንዲረዱት ከተደረገ በኂላ ሟቹ የኔን ባጃጅ በመሰባበር በንብረቴ ላይ ጉዳት በማድረሱ ለፖሊስ አመልካቼ ፖሊስ ተመድቦልኝ ጉዳት አድራሹን ለማሳየትና ለመያዝ ሲባል ከፖሊሶች ጋር ሄድኩኝ እንጂ ይህ ወንጀል እንዲፈፀም ያደረግኩት ተሳትፎ የሌለ በመሆኑ የወንጀል ድርጊቱን አልፈጸምኩም፤ጥፋተኛም አደለሁም ብለው ክደው በመከራከራቸው ፍርድ ቤቱ የዓቃቤሕግን ማስረጃ ከሰማ በኂላ በተመሰከረባቸው ልክ በወ/ህ/ቁ 540 ስር እንዲከላከሉ በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ አመልካች የራስ ተከሳሽነት ቃላቸውና መከላከያ ምስክር አስቀርበው አሰምተዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራቀኙን ማስረጃ ከመረመረ በኂላ የአሁኑ አመልካች ስር 2ኛ ተከሳሽን ሟች ከድር የኑስ የተባለውን ይሔ ነው በሚል በመጠቆም ተከተለው በለው ሲለው ሟች ሲሮጥ ስር 2ኛ ተከሳሽ የሆነው የፖሊስ አባልም ሟችን ተከታትሎ ተኩሶ ሲመታው ሟቹ ሲወድቅ በወደቀበት ቦታ ለሁለተኛ ጊዜ በስተግራ በኩል ደረቱ ላይ በመተኮስ ሟች ከድር የኑስ የገደለው መሆኑን በተጠሪ በኩል ቀርበው በተሰሙት ቀጥተኛ የአይን ምስክሮች የተረመሰከረበት ሲሆን ይህም አመልካች ስር 2ኛ ተከሳሽ ሟችን ተኩሶ እንዲገድል በለው በማለት በማነሳሳቱ ወንጀል ህግ አንቀጽ 36 መሰረት በማነሳሳት የወንጀል ተሳትፎ የነበረው መሆኑን የተመሰከረ ሲሆን የአመልካች መከላከያ ምስክሮች ተጠሪ በሆነው በዓቃቤሕግ በኩል የቀረበባቸውን ቀጥተኛ የዓይን ማስረጃ ማስተባበል የሚችል አይደለም በማለት አመልካች በተከሰሱበት የሕግ አንቀጽ ጥፋተኛ በማለት በሰባት ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡

የአሁኑ አመልካች በተሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘታቸው ይግባኝ ለሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም በመ/ቁ 06073፣06098፣06104 ላይ በቀን 12/03/2015 ዓ.ም በሰጠው

ውሳኔ በስር ፍርድ ቤት በማስረጃ የተረጋገጠው አመልካች መኪና ከሌላ ሰው ተቀበሎ ከፍ/ቤት ወይም ከፖሊስ ህጋዊ መጥሪያ ወይም የመያዣ ትዕዛዝ ሳይኖር ስር 2ኛ ተከሳሽ የሆነው የፖሊስ አባል ሟች በነበረበት ቦታ ወስዶ እሄ ነው በለው በማለት ድርጊቱን እንዲፈፅም ያሳመነ መሆኑን ነው ይህም አመልካች ተራየሰው ግድያ ወንጀል እንዲፈፀም በማነሳሳት የወንጀል ተሳትፎ ማድረጉ የሚያሳይ በመሆኑ በወ/ህግ /ቁ 36 (1) መሰረት አመልካች በተሰሰሰበት ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ መባሉ ተገቢ ነው በማለት ቅጣትን በተመለከተ ሲወስን ስር 2ኛ ተከሳሽ መቀጣት የነበረባቸው በእርከን 28 ስር ሆኖ በዘጠኝ አመት ጽኑ እስራት ሆኖ እያለ ሰባት አመት ጽኑ እስራት መወሰኑ ተገቢ አደለም በመሆኑም በዘጠኝ አመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ሲወስን የአሁኑ አመልካች በሚመለከት ግን ጥፋተኛ የተባለው ወንጀሉን እንዲፈጸም አነሳስተዋል በሚል የወ/ህግ/ቁ 36 መሰረት በማድረግ ሲሆን በስር ፍርድ ቤት ከተረጋገጠው የወንጀል ድርጊት አፈጻጸም አንጻር ሲታይ ስር 2ኛ ተከሳሽ በተኮሰው ጥይት ሟች በመጀመሪያ ተመቶ ሲወድቅ ሟች በወደቀበት ቦታ ለሁለተኛ ግዜ በደረቱ ላይ የተኮሰበት ሲሆን ለ2ኛ ጊዜ ተኩሶ ሟችን መግደሉ በአመልካች የተፈለገ ውጤት መሆኑን የሚያጠራጠር ሆኖ ስላገኘነው በወ/ህ/ቁ 36(3-4) እና 179 (ሐ) መሰረት የአመልካች ቅጣት መሻሻል ያለበት በመሆኑ በዚህ መሰረት አመልካች ለወደፊት ሊያስተምር ይችላል ብለን ያሰብናውን በወ/መ/ህግ 36(3-4) እና 179(ሐ) መሰረት የ7 ዓመት እስራት ሊቀጣ ይገባል በማለት በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ የሰጠው ቅጣት ውሳኔ ስር 2ኛ ተከሳሽ ላይ የተወሰነውን ቅጣት ብቻ ከፍ በማድረግ በዚህ አግባብ ውሳኔውን በማሻሻል በመ/ቁ 06073፣06398፣06104 የሆኑ መዝገቦች በማጣመር ወስኗል፡፡

በመቀጠል አመልካች መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም በሰ/መ/ቁ 00510 በቀን 21/06/2015 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛት አቤቱታቸውን ውድቅ አድርጎታል፡፡

አመልካች ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በቀን 21/09/2015 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት አቤቱታ ይዘቱ ሲታይ፡- ሟቹ የኔን ባጀጅ በመሰባበር በንብረቴ ላይ ጉዳት ያደረሰብኝ በመሆኑ ምክንያት ለፖሊስ አካላት አመልክቼ ፖሊስ ታዞልኝና የመያዣ ትዕዛዝ ይዘው ጉዳት አድርሹን ለመያዝ ወይም ለመጠቆም ሲባል ከፖሊሶች ጋር ሔድኩኝ እንጅ ይህ ወንጀል እንዲፈፀም ያደረኩት አንዳችም ማነሳሳትም ሆነ የሰጠሁትም ተስፋ የለም፡፡ በማናቸውም በድንጋጌው ላይ የተቀመጠውን ሁኔታዎች ባመላከተ ሁኔታ የፈፀምኩት ነገር የለም፡፡ በተጠሪ በኩል ቀርበው በተሰሙት ምስክሮችም አመልካች የወ/ህግ አንቀፅ 36 ስር ስለተገለጹት ሁኔታዎች ስለመፈፀሜ ባልመሰከሩበት ሁኔታ ጥፋተኛ መበሌ ተገቢ አይደለም፤ አመልካች ፖሊስም አይደለሁም፤ የፖሊስ አዛዥም አይደለሁም፤ አመልካች ፖሊስን በለው ስላለው ነው ፖሊስ ተኩሶ የመታው መባሉ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

መሰረታዊ ስህተት ነው፡፡ እንዲሁም የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመከላከያ ማስረጃ አቅርቤ ያስመሰከርኩና በአግባቡ የተከላከልኩ ሆኖ እያለ የዐ/ህግ ምስክሮችም ሆነ የሰነድ ማስረጃዎች ስለ አመልካች ጥፋት/ድርጊት ያሉት ነገር በሌለበት ሁኔታ ጥፋተኛ መባሌ ሊታረም የሚገባ ነው፡፡ ጥፋተኛ ነህ ብባል እንኳ በወ/ህግ 540 መሰረት የፈፀምኩት ግድያ ተግባር ወይም ድርጊት በሌለበት ሁኔታ በግድያ ወንጀል ጥፋተኛ ልባል አይገባም፡፡ በመሆኑም በነፃ እንድሰናበት ይወሰንልኝ፤ ጥፋተኛ ነክ የሚባል ከሆነ ደግሞ ቅጣቱ ቀሎልኝ በገደብ እንዲሆንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም አመልካች ያቀረበውን አቤቱታ እና በስር ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ በመመርመር አመልካች የወ/ሕግ አንቀፅ 32(1) ሀ፤ 33፤ 36(ሀ) እና 540 በመተላለፍ ስር 2ኛ ተከሳሽ የሆነውን የፖሊስ አባል የግድያ ወንጀል እንዲፈጸም አነሳስቷል በሚል ጥፋተኛተብሎ በሰባት ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጡ የመወሰን አግባብነት የወንጀሉ አፈፃፀም፤ በአመልካች ተነሳስቶ ግድያ ወንጀል ፈፀመ የተባለው ስር 2ኛ ተከሳሽ ፖሊስ መሆኑ ካለው የስራ ኃላፊነት አንጻር የወንጀል ህጉ አንቀፅ 36 አተገባበር ረገድ የሚኖረው ውጤት እንዲሁም ወ/ህግ/ አንቀጽ 2፤23/2 ድንጋጌዎችና በሰ/መ/ቁ 38161፤ 91535፤75387 ከተሰጡት ውሳኔዎች አንጻር ተጠሪ ባለበት ለመመርመር ሲባል በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 2(4) (ሸ) እና 10 /1(ሐ) እንዲሁም በሰበር ሰሚ ስን-ስርዓት መመሪያ ቁጥር 12/2015 ዓ.ም አንቀፅ 7/3 መሰረት ተጠሪ በጉዳዩ ላይ መልስ እንዲሰጥበት አዟል፡፡

ተጠሪም በቀን 29/-8/2016 ዓ.ም የተፃፈ መልስ ሰጥቷል፡፡ በመልሱም የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ማስረጃ በአግባቡ መዝኖ የሰጠው ውሳኔ አግባብነት ያለው በመሆኑ ምንም አይነት መሰረታዊ የህግ ስህተት የለውም፡፡ የወንጀል አፈጻጸሙ ሲታይ ፖሊስ ካለው የስራ ሃላፊነት አንጻር ምንም ህጋዊ መጥሪያና የመያዣ ትዕዛዝ በሌለበት በአንድ ተራ ሰው ያዝልኝ ምታልኝ ትዕዛዝ ወይም ስምምነት ድርጊቱን ፈጽሞ እያለ አመልካች ያቀረበው ቅሬታ በማስረጃ ያላስደገፈ በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶቹ በየደረጃው የሰጡት ውሳኔ አግባብነት ያለው ነው፡፡ በሌላ በኩል የዐ/ህግ ክስ የወ/ህግ አንቀጽ 23 ስር የተዘረዘረውን የሚያሟላና ግልፅ የሆነ ዐ/ህግ ክሱን በማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ ፍ/ቤቱ የሰጠው ውሳኔ አግባብ ነው በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካችም በቀን 09/09/2016 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተገለፀውን የሚመስል በዚህ ጉዳይ አንድ ግለሰብ ለፖሊስ ሚቼን በለው ሲለው ፖሊሱ ሚቹን ቢገድለው ግለሰቡ የፖሊስ አባሉ የግድያ ወንጀል እንዲፈጽም አነሳስተዋል ለማለት ይቻላል ወይ የሚለው ፖሊስ ካለው የስራ ሀላፊነት አንጻር የአመልካቹ ድርጊት የወንጀል ህጉ አንቀፅ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

36 የተመለከተውን የማነሳሳት ተግባር ሊያሚላ የሚችል ነው ሊባል የሚችል ነው ወይስ አደለም የሚለው በዚህ ችሎት ምላሽ ሊያገኝ የሚገባው የክርክሩ መሠረታዊ ጭብጥ ነው፡፡

በመሠረቱ አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ህጋዊ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሚልተው ሲገኙ ብቻ መሆኑን በአዋጅ ቁጥር 414/1996 የወንጀል ህጉ አንቀፅ 23(2በግልፅ ተደንግጓል፡፡ እንግዲህ አንድን ድርጊት ወንጀል ነው ብሎ ለመወሰን ህጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች ተጣምረው መገኘት የግድ ይላል፡፡ ህጋዊ ፍሬነገር የሚባለዉ አንድን ድርጊት ህገወጥነትና አስቀጭነት ወንጀል ስለመሆኑ በህግ በግልጽ ተደንግጎ መገኘት ያለበት ስለመሆኑ፣ግዙፋዊ የሚባለዉ በህጉ የተደነገዉ የወንጀሉ ማቋቋሚያ ድርጊት ማለት በህግ የተከለከለዉን ማድረግ ወይም በህግ የታዘዘዉን አለማድረግ /አል-ድርጊት/ ፍሬነገሮች መፈጸማቸዉና የተፈጸሙትም በተከሳሹ ስለመሆኑ መረጋገጥ እና የሞራል /ሀሳብ/ ክፍል የሚባለዉ ተከሳሹ ድርጊቱን አስቦ ወይም በቸልተኛነት የፈጸመ መሆኑ የማረጋገጥ ጉዳይ የሚመለከት ስለመሆኑ ከወንጀል ህጉ አንቀጽ/2/፣23/1/እና 57/1/ ድንጋጌዎች ይዘት የሚያሥገነዝቡን ጉዳይ ነዉ፡፡ በሌላ በኩል በአንድ የወንጀል ድርጊት ላይ ከአንድ በላይ ተከሳሾች ተካፋይ የሆኑ እንደሆነ የእያንዳንዱ ተከሳሽ ተሳትፎ/የተካፋይነት/ ደረጃ ተለይቶ መረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑም የወንጀል ህጉ አንቀጽ 32 እስከ 41 ያሉት ድንጋጌዎች ይህንኑ የሚያመለክቱ ናቸው፡፡

ተጠሪ አመልካች በክሱ በተጠቀሰዉ የወንጀል ድርጊት ስላለዉ ተካፋይነት ለመግለጽ የወንጀል ሕጉን

አንቀጽ 32(1/ሀ)፣33 እና 36(ለ) ድንጋጌዎች ላይ የተመለከተዉን በመጥቀስ ክስ መስርቶበታል፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች አንድ ወንጀል ፈጻሚ በወንጀል አፈጻጸም ላይ ተካፋይ ሊሆን የሚችልባቸዉን የተካፋይነት አይነትና ደረጃ የሚደነግጉ ናቸዉ፡፡ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32 እና ተከታዮቹ ላይ ከተመለከተዉ መረዳት እንደሚቻለዉ አንድ የወንጀል ድርጊት በአንድ ሰዉ ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ(ብዙ) ሰዎች ተሳትፈዉበት ሊፈጸም ይችላል፡፡ በብዙ ሰዎች የተፈጸመ ወንጀል በሆነ ጊዜ የወንጀል ፈጻሚዎቹ ተሳትፎ ደረጃ አንድ አይነት ወይም የተለያየ ሊሆን ይችላል፡፡ በወንጀሉ አፈጻጸም ያላቸዉ ተካፋይነት አንድ አይነት ነዉ ወይስ የተለያየ የሚለዉን ለመለየት የተከፋይነታቸዉን አይነት፣ ደረጃ እና በወንጀሉ አፈጻጸም የነበራቸዉን ሚና መለየት ይገባል፡፡

ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32 እና ተከታዮቹ መገንዘብ እንደሚቻለዉ የወንጀል ድርጊቱን በቀጥታ(በራሱ) የፈጸመም ሆነ በራሱ ድርጊቱን ባይፈጽምም የወንጀል ድርጊቱንና የሚያስከትለዉን ዉጤት የራሱ በማድረግ በሀሳብ ወይም በሌላ ሁኔታ ተካፋይ የሆነ ሰዉ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተከፋይ እንደሆነ እንሚቆጠር  በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32/1 ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል ፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ማንም ሰዉ በአንቀጽ 32/1 ስር ከተደነገጉት ሁኔታዎች በአንዱ ዘዴ በቀጥታ ወይም በእጅ አዙር ወንጀሉን አድርጎ እንደሆነ ወይም ወንጀሉን እርሱ ራሱ በቀጥታ ባያደርግም እንኳን በመላ አሳቡና አድራጎቱ በወንጀሉ ደርጊትና በሚሰጠዉ ዉጤት ሙሉ ተካፋይ በመሆን ድርጊቱን የራሱ ያደረገ እንደሆነ በመጀመሪያ ደረጃ ዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ እንደሆነ እንደሚቆጠር በሌላ በኩል ማንኛዉም ሰዉ በሁለተኛ ደረጃ ዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ ሆኗል ሊባል የሚችለዉ በቀጥታ ወንጀል ድርጊቱን በራሱ ባይፈጽምም በመጀመሪያ ደረጃ ዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ወንጀሉን የሚፈጽመዉን ሰዉ ወንጀሉ ከመፈጸሙ በፊት ወይም ወንጀሉ በሚፈጸምበት ሂደትና ጊዜ በመነትነት ፣ወሬ በማቀበል፣በመምክር፣ ወንጀል የሚደረግበትን ዘዴ ወይም ገንዘብ፣ መሳሪያ ወይም ግዙፋዊ እርዳታ ወይም ስጦታ በመስጠት ወይም ለወንጀሉ አፈጻጸም በሚጠቅም በማናቸዉም ሌላ አይነት መንገድ ወይም ዘዴ አንድ ወንጀል እንዲደረግ በማነሳሳት፤በማግባባት ወይም በማበረታታት የተሳተፈ እንደሆነ መሆኑን (የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 36 እና 37 ይመለከቷል) ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 228017 ላይ በዚህ አግባብ  የሕግ ትርጉም ተሰጥቷል፡፡

በወንጀል ጉዳይ የሚሰጥ ውሳኔ በተከሳሹ ነጻነት ወይም ሕይወት ላይ የሚሰጥ ውሳኔ በመሆኑ በአንድ የወንጀል ጉዳይ የሚቀርብ ማስረጃ በቂና አሣማኝ በሆነ ሁኔታ የወንጀል ድርጊቱ መፈፀሙንና የወንጀል ድርጊቱን ፈፃሚ ማንነት በትክክል ለይቶ ማሳየት ያለበት ስለመሆኑ እና ከሳሽ የሆነው አቃቤ ሕጉም ይህንኑ በሕጉ የተጣለበትን ግዴታ መወጣት ያለበት ስለመሆኑ ከወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 141 ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ፍ/ቤቱ ተከሳሹ እንዲከላከል ብይን ሊሰጥ የሚችለውም ዓቃቤሕግ ባቀረባቸው ማሥረጃዎች ተከሳሹ ወንጀል መፈፀሙን ተፈፀመ የተባለው ወንጀል ደግሞ በተከሳሹ መፈፀሙ በበቂና በአሳማኝ ሁኔታ ያረጋገጡ ሆነው ባገኛቸው ጊዜ ስለመሆኑ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23 (2)እና(4)፤57፤58(1) እና ከወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 141 እና 142 ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ዓቃቤሕግ ወንጀሉ በተከሳሽ የተፈጸመ ለመሆኑ ለማሥረዳት ባቀረበው በቂ እና አሣማኝ ማስረጃ እንደክሱ ያስረዳ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ተከሳሽ ክሱን እንዲከላከል ብይን ተሰጥቶ ባቀረባቸው ማሥረጃዎች ክሱን ያላስተባበለ እንደሆነ ፍ/ቤቱ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 149 መሠረት በተከሳሽ ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ እንደሚሰጥ በግልጽ በስነስርኣት ህጉ ላይ ተደንግጓል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች በተከሰሰበት የተራ ግድያ ወንጀል ጥፋተኛ ሊባል የቻለው ስር 2ኛ ተከሳሽ የሆነውን ፖሊስ አባል ሚች ሲሮጥ በለው በማለት በማነሳሳቱ ምክንያት ስር 2ኛ ተከሳሽ ሚችን ተኩሶ ሊገድል ችሏል በሚል ነው፡፡

ማንም ሰው ወንጀል እንዲደረግ አነሳሳ የሚባለው አስቦ ሌላውን ሰው በመጎትጎት ተስፋ በመስጠት፣ በገንዘብ፣ በስጦታ፣በማስፈራራት ወይም በማናቸውም ሌላ ዘዴ አንድ ወንጀል እንዲያደርግ ያግባባ እንደሆነ መሆኑን የወንጀል ህጉ አንቀጽ 36(1) የሚደነግግ ሲሆን ዋና ወንጀል አድራጊው ያደረገው ወንጀል፣ አነሳሹ ከፈለገው በላይ በሆነ ጊዜ አነሳሹ የሚቀጣው እርሱ በፈለገው ወይም ይሆናል ብሎ ሊገምተው በሚችለው ወንጀል ብቻ መሆኑን በወንጀል ህግ አንቀጽ 58(3)፤ ይህም የሚሆንበት ጊዜ ዋና ወንጀል አድራጊው ላደረገው ከባድ ወንጀል እርሱ ብቻ ሀላፊ ሆኖ ይቀጣል በማለት በዚሁ ድንጋጌ ንኡስ አንቀጽ 4 ስር ተመልክቷል፡፡

አመልካች ሚች በንብረቴ ላይ ጉዳት አድርሷል በሚል ስር 2ኛ ተከሳሽ የሆነው የፖሊስ አባል ጋር በመሆን ሚችን ሲያፈላልጉ ሚችን ሲያገኙው የፖሊስ አባሉን ይሄውና በንብረቴ ላይ ጉዳት ያደረሰው ሰው በሚል በመጠቆም ሚችን ሊይዙት ሲሉ በመሮጡ አመልካች የፖሊስ አባል የሆነውን ስር 2ኛ ተከሳሽን ሚችን በለው ሲለው ሁለቴ በጥይት ተኩሶ ሚቹን ሊገድለው መቻሉን ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች ተረጋገጧል፡፡ እዚህ ላይ አከራካሪው ነጥብ አመልካች ስር 2ኛ ተከሳሽ የሆነው ፖሊስ አባል ሚችን በለው ሲለው ፖሊስ አባሉ ሚችን ሁለቴ ተኩሶ መግደሉ አመልካች ለፖሊስ አባሉ ሚችን በለው ማለቱ እንደሚታወቀው ፖሊስ የዜጎችን ሰላምና ፀጥታ ለማስከበር ዘብ የቆመ፤ በወንጀል የተጠረጠረ ሰው እንዴት በቁጥጥር ስር ማድረግ እንዳለበት ያውቃል ተብሎ የሚገመት ሰው፤ አመልካች ሚችን በለው በማለቱ የፖሊስ አባሉ ሚችን እንዲገድለው አነሳስቷል  ለማለት የማይቻልና አመልካች ወንጀሉን እርሱ ራሱ በቀጥታ ቢያደርግ ወይም በቀጥታ ባያደርግም እንኳን በመላ ሐሳቡና አድራጐቱ በወንጀሉ ድርጊትና በሚሰጠው ውጤት ሙሉ ተከፋይ በመሆን ወንጀሉን የራሱ ያደረገ መሆኑን የሚያሳይ አይደለም፡፡ የፖሊስ አባሉ ካለው የስራ ሀላፊነትና ህግን የማስከበር ትልቅ ሀላፊነት አንጻር አመልካች በለው ስላለ አንድን ሰው ተኩሶ ይገድላል ተብሎ የሚታሰብ ባለመሆኑ፤ ስርተከሳሾቹ በአድራጎታቸው እና አድራጎታቸው በሚያመጣው ውጤት ላይ በተከሳሾች መካከል የሐሳብ መስማማት / meeting of minds / የነበረ ስለመሆኑ አያሳይም ይህ ከሆነ ደግሞ የአመልካች ተግባር በወንጀል ህጉ አንቀጽ 36 ስር በተደነገገው መሰረት ሚችን ለመግደል የማንሳሳት ተግባር ፈጽሟል ለማለት አይቻልም፡፡ እንዲሁም አመልካች አስቀድሞ ሚቹን ለመግደል በመላ ሐሳቡና አድራጐቱ በወንጀሉ ድርጊትና በሚሰጠው ውጤት ሙሉ ተከፋይ በመሆን የግድያ ወንጀሉን እንዲፈፀም በማነሳሳት ወንጀሉን የራሱ ያደረገ ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ በስር ፍርድ ቤቶች አመልካች ተራ የግድያ ወንጀል እንዲፈፀም አነሳስቷል በማለት በተከሰሰበት ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ መባሉ ከወንጀል ህግ አንቀጽ 36 አተገባበር አንጻር እንዲሁም የወንጀል ህጉ አንቀጽ 2፤23/2፣57 እና 58 (3) ድንጋጌዎች የሚጥስና በመሆኑ በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

1234/2013 2(4) እና 10/1(ሐ)እና(መ) ላይ ከተቀመጡት መመዘኛዎች አንጻር መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች በአመልካች ላይ ያስተላለፉትን የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በመሻር አመልካች በነጻ እንዲሰናበት በማለት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1. በሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 21652፣ ሚያዝያ 11 ቀን 2014 ዓ.ም አመልካችን ጥፋተኛ በማለት፣ ሚያዝያ 17 ቀን 2014ዓ.ም በአመልካች ላይ የሰጠው የቅጣት ውሳኔ፣ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 06073፣ 06098 እና 06104 የሆኑ መዝገቦች በማጣመር አመልካችን በሚመለከት ህዳር 12 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ በማጽናት አመልካችን በሚመለከት በመ.ቁ 00510፣ የካቲት 21 ቀን 2015ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 መሰረት ተሽረዋል፡፡

2. ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት አመልካች ከተከሰሰበት ወንጀል ክስ በነጻ እንዲሰናበት ተወስኗል፡፡

ትዕዛዝ

- የሚመለከተው ማረሚያ ቤት አመልካች በነጻ የተሰናበተ መሆኑን አውቆ ከእስር እንዲፈታው የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ይድረሰው፤
- የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይድረሳቸው፡፡
- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፍ/ደ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ. 247605

ጥቅምት 5 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

ሰናይት አድነው

ሀፊዝ አባጀማል

አመልካች- ወ/ሮ ውባለም አሻግሬ ቀረቡ

ተጠሪዎች- 1. አቶ ጉዲሳ ቢቂላ ቦኮን
2. ወ/ሮ ድንቂቱ ሁንዴ
3.ወ/ሮ አለም ጉዲሳ
4.አቶ ተስፋዬ ጉዲሳ
5.አቶ ሮቢ ጉዲሳ
} አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የስጦታ ውል እንዲፈርስ የቀረበ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የጀመረውም በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር አመልካች ከሳሽ፣ ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ነሐሴ 20 ቀን 2013 ዓ.ም ባቀረቡት ክስ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ከ1988 ዓ.ም እስከ 1998 ዓ.ም ድረስ እንደባል እና ሚስት እንዲሁም

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ በባህላዊ መንገድ ጋብቻ ፈጽመን አብረን ስንኖር በጋራ ያፈራነውን ንብረት አመልካች ባላወቅኩበትና ባልፈቀድኩበት ሁኔታ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ከ3ኛ እስከ 5ኛ ካሉት ተጠሪዎች ጋር በመመሳጠር የአመልካችን እውቅናና ፍቃድ ሳያገኙ ጳጉሜ 2 ቀን 2009 ዓ.ም የአመልካችን ድርሻ ጨምረው በ240 ካ.ሜ ላይ ያረፈ ቤትና ይዞታ ላይ ያደረጉት የስጦታ ውል ይፍረስልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪዎች ታህሳስ 07 ቀን 2014 ዓ.ም በሰጡት መልስ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማስቀደም የተከራከሩ ሲሆን፣ የመጀመሪያ መቃወሚያቸዉም ጳጉሜ 2 ቀን 2009 ዓ.ም የተደረገው የስጦታ ውል እንዲፈርስላቸው አመልካች የጠየቁት ዳኝነት በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 69 መሰረት በይርጋ ይታገዳል የሚል ነዉ፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤትም በመቃወሚያው ላይ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኂላ የስጦታ ውል እንዲፈርስ ክስ መቅረብ ያለበት በማናቸውም ሁኔታ ውል በተደረገበት በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ በመሆኑና ክስ የቀረበው የስጦታ ውሉ ከተደረገ ሁለት ዓመት ካለፈው በኃላ በመሆኑ በተሻሻላው የፌዴራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀስ 69 መሰረት ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት ክሱን በብይን ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ውሳኔ ቅር የተሰኙት አመልካች ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ የስር ፍርድ ቤቱን ውሳኔን በማጽናት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ግንቦት 3 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት 3 ገጽ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ተፈፅመዋል ያሏቸውን ስህተቶች በመዘርዘር በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲታረሙላቸዉ ጠይቀዋል፡፡ የአቤቱታዉ ይዘትም በአጭሩ 1ኛ ተጠሪ ስጦታውን የራሱ ባልሆነ እና በአመልካች ድርሻ ላይ የሰጠ ሲሆን በፍ/ብ/ህ/ቁ 2427 እና 1845 እንዲሁም በሰ/መ/ቁ 105652 በተሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም አግባብ አንድ ሰው የራሱ ያልሆነን ንብረት በስጦታ ለሌላ ሰው ለመስጠት የማይችል ከመሆኑ አኳያ የስጦታ ዉል ይፍረስልኝ ዳኝነት ይርጋ 10 ዓመት ነዉ፤ ለክርክር መነሻ የሆነውን ንብረት ከ1988 ዓ.ም ጀምሮ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ በተለያዩ ጊዜያት ግንባታ እያከናወንን ቤቶች ሰርተንበት ስንጠቀምበት የቆየን እና ስጦታው ተሰጠ ከተባለበት 2009 ዓ.ም በኂላም በሁለታችን እጅ የሚገኝ ሆኖ ሳለ ክሱ በይርጋ ይቋረጣል በማለት የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ አግባብነት የሌለውና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል የሚል ነው፡፡

የሰበር አቤቱታዉም ተመርምሮም ለክርክሩ መነሻ የሆነው ክስ በሁለት አመት ይርጋ ይታገዳል ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ግራ ቀኝ በተገኙበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል ተብሏል፡፡ በዚሁም መሠረት ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ በሰጡት መልስ አመልካች የፍትሐብሔር ህጉን አንቀጽ 2427 እና 1845 ጋር በማጣመር የሚያቀርቡት ክርክር በስር ፍርድ ቤት ያልተነሳ፣ ግራ ቀኝ ያልተከራከርንበት እና በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ያልተሰጠበት አዲስ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ክርክር በመሆኑ ውድቅ ሊደረግ ይገባል፡፡ አመልካች መብታቸውን መጠየቅ የሚችሉት የውሉን መኖር ካወቁ በኃላ ሳይሆን ውል ከተደረገበት ቀን ጀምሮ መሆን ይገባዋል፡፡ አመልካች የስጦታ ዉል መደረጉን ካወቁ ከስድስት ወር በኃላ ያቀረቡት የውል ይፍረስልኝ ክስ በይርጋ የታገደ ነው በሚል የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ እንዲፀና በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታቸዉን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል ይህ ችሎትም የአመልካችን የሠበር አቤቱታ በዚህ ችሎት ከተያዘው ጭብጥ፣ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ለጠየቁት ዳኝነት መሠረት ያደረጉት ያለ እርሳቸዉ ዕዉቅና እና ስምምነት የጋራቸዉ በሆነ ንብረት ላይ በ1ኛ ተጠሪ የተደረገ የስጦታ ዉል እንዲፈርስ ሲሆን፣ ተጠሪዎች በበኩላቸዉ ዳኝነቱ በይርጋ ሊታገድ ይገባዋል በማለት የሚከራከሩት ዉሉ የተደረገዉ በ2009 ዓ.ም መሆኑን በመጥቀስ ነዉ፡፡ ለዳኝነቱ ምክንያት የሆነዉ ዉል የተደረገዉ ጳጉሜ 2009 ዓ.ም ስለመሆኑ ያላከራከረ ሲሆን፣ ክሱ የቀረበዉ ነሐሴ 20 ቀን 2013 ዓ.ም ነዉ፡፡ ከላይ እንደተመለከተዉ የስር ፍርድ ቤት ክሱ በይርጋ ይታገዳል በሚል ሲወስን መሠረት ያደረገዉ አመልካች ዉሉ እንዲፈርስ ዉሉ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ ቢበዛ በሁለት ዓመት ጊዜ ዉስጥ አላቀረቡም በሚል የፌዴራል የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 69ን በዋቢነት በመጥቀስ ስለመሆኑ የዉሳኔዉ ይዘት ያሳያል፡፡

በርግጥ በተጠቀሰዉ የቤተሰብ ህጉ ድንጋጌ ከባልና ሚስት ያለ አንደኛዉ ተጋቢ ፈቃድ ወይም ስምምነት የተደረገ ዉል እንዲፈርስ የሚቀርብ ዳኝነት ጥያቄ ዉሉ መደረጉ ከታወቀበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወር ጊዜ ዉስጥ ሆኖ በማንኛዉም ሁኔታ ዉሉ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ በሁለት ዓመት ጊዜ ዉስጥ መቅረብ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ይሁንና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 105652 ላይ በሰጠዉ ዉሳኔ ከባልና ሚስት አንደኛዉ ተጋቢ ያለ ሌላኛዉ ተጋቢ ፈቃድ ወይም ስምምነት የተደረገ የስጦታ ዉል እንዲፈርስ የሚቀርብ የዳኝነት ጥያቄን አስመልክቶ ተፈፃሚነት ያለዉ የይርጋ ድንጋጌ የስጦታ ዉልን ልዩ ባህሪ መሠረት ያደረገ ሊሆን ይገባል የሚል ምክንያት በመስጠት፣ ተፈፃሚነት ያለዉ በቤተሰብ ህጉ ላይ የተመለከተዉ ሳይሆን በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1845 ላይ የተመለከተዉ የአስር ዓመት የይርጋ ጊዜ ሊሆን እንደሚገባ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ ይህ የህግ ትርጉም በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10(2) መሠረት ለተያዘዉ ጉዳይ ተፈፃሚነት አለዉ፡፡ በመሆኑም የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ በፌዴራል የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 69 መሠረት በይርጋ ይታገዳል በማለት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የጸናዉ ብይን ከፍ ሲል የተመለከተዉን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ ያገናዘበ ባለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4-ሸ) እና አንቀጽ 10(1-ሀ) መሠረት መታረም የሚገባዉ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

## ዉሳኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 99382 ላይ ጥር 13 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 286297 ላይ የካቲት 06 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተዘግቶ የነበረዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ በፍሬ ነገሩ ላይ አከራክሮ ተገቢዉን ዉሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩ በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 9(2) መሠረት ተመልሶለታል፡፡
3. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፍ/ደ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ሰ.መ.ቁ 247682
ጥቅምት 05 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው
በዕውቀት በላይ
ቀነዓ ቂጣታ
ብርሃኑ መንግስቱ
ማርታ ተካ

አመልካች፡- ዳግማዊ አረጋው -አልቀረቡም

ተጠሪ፡- በፍትህ ሚኒስቴር ስር የፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ -ተመስገን በላይነህ -ቀረቡ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡

በመሆኑም በክረምት ስራ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍርድ**

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ግንቦት 21 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 285713፤ ጥር 04 ቀን 2015 ዓ.ም በአመልካች ላይ ያስተላለፈው የጥፋተኝነት ውሳኔም ሆነ ጥር 18 ቀን 2015ዓ.ም ያስተላለፈው የቅጣት ውሳኔ እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 242076 በስር የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ በማጽናት የቅጣት ውሳኔው በማሻሻል ግንቦት 09 ቀን 2015ዓ.ም የሰጠው

ማስታወሻ፡ - ይህ የ ሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነ ድ ለ ጥና ትና ምር ምር ሥራ ወይምለ ግን ዛ ቤ እ ን ጂ ለ ፍርድ አ ፈጻጸ ምዓላ ማአ ያ ገ ለ ግልም!

ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

ጉዳዩ ከባድ ግድያ ወንጀል ተፈጽሟል ተብሎ የቀረበን ክስ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ በስር ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 539(1)ሀ ድንጋጌን በመተላለፍ ሰውን ለመግደል በማሰብ ታህሳስ 30 ቀን 2014ዓ.ም ከሌሊቱ በግምት 9፡00 እስከ 10፡00 ሰኣት ውስጥ በአራዳ ክከተማ ወረዳ 04 ክልል ልዩ ቦታው ሳሬም ሆቴል ጀርባ ባለው መኖሪያ ቤት ውስጥ በፍቅር ግንኙነት አብራው የምትኖረውን ሚች ሰብለ ንጉሴን ያገዳደሉ ሁኔታ ጨካኝነትን እና ነውረኝነትን በሚያሳይ ሁኔታ በእጁ ይዞት በነበረው የቤት ቁልፍ በመምታት፣ ግንባሯ ላይ ደጋግሞ በጥፊ ፊቷን በመምታት፣በቢላ የግራ እግሯ ታችኛው ክፍል ወይም መርገጫ እግሯን እና የቀኝ እጅ ትንሽ ጣት ላይ በመውጋት ጥልቀት የሌለው የቆዳ መቆረጥ እንዲደርስባት በማድረግ እንዲሁም ሳኒታይዘር ሰውነቷ ላይ በማርከፍከፍ ክብሪት ለኩሶ በማቃጠል ፊቷ፣ አንገቷ፣ የደረት ሦስተኛ ክፍል፣ ሆዷ፣ እጆቿ እና እግሮቿ በእሳት እንዲቃጠሉ በማድረግ አብዛኛው የሰውነት ክፍሏ በመቃጠሉ እና ቁስሉ ኢንፌክሽን ፈጥሮ ወደ ሳምባዋ እና አእምሮዋ ተዛምቶ የደም ዝውውሯ እና የትንፋሽ ሥርዓቷ በመቋረጡ ሕይወቷ እንዲያልፍ ያደረገ በመሆኑ በፈፀመው ከባድ የሰው ግድያ ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

አመልካች ክሱ ተነቦለት እንዲረዳው ከተደረገ በኃላ ያቀረበው መቃወሚያ በብይን ታልፎ የእምነት ክሕደት ቃሉ ሲጠየቅ ድረጊቱን አልፈጸምኩም፤ ጥፋተኛም አደለሁም ብሎ ክዶ በመከራከሩ ፍርድ ቤቱ ተጠሪ በሆነው ዓቃቤሕግ በኩል ቀርበው የተሰሙት የዘጠኝ ምስክሮች ቃልና የሰነድ ማስረጃዎች ጋር መርምሮ አመልካች የቀረበበትን ክስ እንዲከላከል ሲል ብይን ሰጥቷል፡፡ አመልካች በኩል አንድ መከላከያ ምስክር አቅርቦ እንዳሰማ በፍርዱ በማስፈር አመልካች አንድ መከላከያ ምስክር ያሰማና በፍርድ ቤት ትእዛዝ የተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎች እንዲቀርብለት ያደረገ ቢሆንም ያቀረባቸው ማስረጃዎች ድርጊቱ ከተፈፀመ በኃላ ስላለው ሁኔታ ከሚያስረዱ በስተቀር አመልካች የተከሰሰበት የወንጀል ድርጊት አለመፈፀሙን የሚያስረዱ ስላልሆኑ የቀረበበትን ክስ አልተከላከለም በማለት አመልካች በተከሰሰበት ወንጀል ሕግ አንቀጽ ስር ጥፋተኛ በማለት በሞት ቅጣት እንዲቀጣ ሲል ወስኗል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ በማለቱ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም በመ/ቁ 242076 ግራቀኙን አከራክሮ ግንቦት 11 ቀን 2015ዓ.ም ሲወስን ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት አንድ መከላከያ ምስክር ብቻ ማሰማቱን በፍርድ ሀተታ ላይ በማስፈር ባሰማው አንድ መከላከያ ምስክርም ሆነ የሰነድ ማስረጃዎች በተጠሪ የቀረበበትን ክስና ማስረጃ የሚያስተባብሉ ስላሆኑ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች በተከሰሰበት ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ ማለቱ ተገቢ ነው በማለት በስር ፍርድ ቤት አመልካች ጥፋተኛ በማለት የሰጠው ውሳኔ በማጽናት ሲወስን፤ ቅጣቱን በሚመለከት ግን አመልካች ሁለት ማቅለያ ምክንያት ተይዞለት ሊቀጣ የሚገባው በሞት ቅጣት ሳይሆን በ25 አመት ጽኑ እስራት ቅጣት ሊሆን ይገባል በሚል የቅጣት ውሳኔውን ብቻ በማሻሻል ወስኗል፡፡

አመልካች ግንቦት 21 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፎ ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ይዘቱ ሲታይ፡- የስር ፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዓቃቤሕግ ምስክሮች ተሰምተው ተከላከል ከተባልኩ በኃላ የራስ ተከሳሽነት ቃሌን በመስጠት አምስት መከላከያ ምስክሮች አቅርቤ አሰምቼ እያለሁ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ሆነ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት አንድ መከላከያ ምስክር ብቻ እንዳቀረብኩ ተቆጥሮ የሰጠሁት የተከሳሽነት ቃሌንና በ16/12/2014ዓ.ም ቀርበው የተሰሙት አራቱ መከላከያ ምስክሮቼ የሰጡት የምስክርነት ቃል በሰጡት ፍርድ ሳያካትቱ መወሰናቸው ማስረጃዎቼ ሳይመዘኑ መወሰናቸው የሚያሳይ በመሆኑ የሰጡት ፍርድ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው እንዲሁም ቅጣት ሲወስን ያደረግኩት የሟችን ህይወት ለማትረፍ ያደረግኩት አስተዋጽኦ፤ የልጅ አባት መሆኔ እና የጤናዬ ሁኔታ አስመልክቶ ያቀረብኳቸው ሶስት ማቅለያ ምክንያቶች ውድቅ መደረጋቸው ተገቢ ባለመሆኑ በአጠቃላይ ያቀረብኳቸው አምስት ማቅለያ ምክንያቶች ተይዘው ቅጣቱ ሊወሰን ሲገባ ሁለት ማቅለያ ምክንያት ብቻ ተይዞ በ25 አመት ጽኑ እስራት እንድቀጣ መወሰኑ ተገቢ ባለመሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች በአመልካች ላይ የተላለፈው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ አመልካች በ16/4/2014ዓ.ም በዋለው ችሎት አራት ምስክሮች፤ በ3/2/2015ዓ.ም በዋለው ችሎት አንድ ምስክር አጠቃላይ አምስት የሰው መከላከያ ምስክሮች ማሰማቱን የስር ፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገብ የሚያሳይ ሆኖ እያለ በስር ፍርድ ቤት ፍርድ ሀተታ አመልካች አንድ መከላከያ ምስክር ብቻ አቅርቦ ማሰማቱን ተጠቅሶ አራቱ መከላከያ ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ቃል ሳይካተት በአመልካች በኩል ቀርበው የተሰሙት መከላከያ ምስክሮች ቃል ሙሉ በሙሉ የማስረጃ ምዘና ባልተደረገበት አመልካች

አልተከላከለም ተብሎ ጥፋተኛ በማለት ቅጣት የመወሰኑን አግባብነት የወንጀል ማስረጃ ምዘና መርህ አተገባበር ጋር በተያያዘ በሰ/መ/ቁ 147246፤172206፤89676 እና በሌሎች በርካታ መዝገቦች ከተሰጡ ገዢ ውሳኔዎች አንጻር ለመመርመር ሲባል ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡

በተጠሪ በኩል ሚያዝያ 28 ቀን 2016ዓ.ም ጽፎ የሰጠው መልስ ይዘቱ ሲታይ፡- አመልካች አምስት መከላከያ ምስክር ያሰማ መሆኑን በማመን የስር ፍርድ ቤቶች ሲወስኑ አንድ መከላከያ ምስክር አቅርቧል ማለታቸው የጽሁፍ ስህተት ሊሆን እንደሚችል ሆኖም በአመልካች የሰጠው የተከሳሽነት ቃልም ሆነ ያሰማቸው መከላከያ ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ቃል በስር ፍርድ ቤቶች በአመልካች ላይ የተላለፉትን የጥፋተኝነት ውሳኔ በውጤት ደረጃ የማይለውጡ እና አመልካች ተከላክሏል የሚያሰኙ ስላልሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት መፈፀሙን አያሳይም፤ ቅጣትን በተመለከተ አመልካች የወንጀል ድርጊቱን አልፈፀምኩም በሚል ክዶ ሲከራከር የቆየና ከጥፋቱ ያልተማረ መሆኑን፤የጤና ሁኔታ በተመለከተ የጥርስ ህመም ያለበት መሆኑ ጠቅሶ በስር ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን የስር ፍርድ ቤቶቹ ከወንጀሉ አፈጻጸም አንጻር የቅጣት ማቅለያ ምክንያት በሚል ያቀረባቸው ፍርድ ቤቶቹን ስላላመኑባቸው አመልካች በማቅለያነት ሊያዙልኝ ይገባ ነበር የሚላቸው ባለመቀበል ለአመልካች እና ለሌሎች ወንጀል ፈጻሚዎች ሊስጠነቅቅ የሚችል የቅጣት ውሳኔ መወሰናቸው የሚያሳይ በአመልካች ላይ የተወሰነው የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት አደለም የሚል ነው፡፡

ይህ ችሎትም ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ ከተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ) ስር እንደተመለከተዉ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠዉ ሥልጣን ማናቸዉንም መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበትን የመጨረሻ ዉሳኔ በሕግ በዝርዝር በሚወሰነዉ አግባብ መርምሮ እንዲያርም ነዉ፡፡ ከዚህ ባለፈ ተከራካሪ ወገኖች ማስረጃ ለመቀበል፣ ለመስማትና ለመመዘን ሥልጣን ለተሰጣቸዉ የስር ፍርድ ቤቶች ያቀረቡትን ማስረጃዎች የመመዘን ጉዳይ ዉስጥ በመግባት ማስረጃዎችን በመመርመርና በመመዘን አከራካሪ የሆነዉ ፍሬነገር መኖር አለመኖሩን ወይም ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል

ፈጽሟል ወይስ አልፈጸመም የሚለዉን በማረጋገጥ ዉሳኔ መስጠት መሰረታዊ የሕግ ስህተት እንደማረም የሚቆጠር ባለመሆኑ  የሰበር ሰሚ ችሎት ሥልጣን አይደለም፡፡

ሆኖም ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን እና በይግባኝ ሰሚነት የሚዳኙ ፍርድ ቤቶች የማስረጃ አቀራረብን፣ አግባብነትን፣ ተቀባይነትን እና ማስረጃ አቅርቦ አንድን ፍሬ ነገር የማስረዳት ሸክም የሚመለከቱ መርሆዎች አተገባበር በሚቃረን አኳኋን እንዲሁም የማስረጃ ምዘናን ወይም የማስረዳት ደረጃን (standards of proof or weight of evidence) የሚመለከቱ መሰረታዊ መርሆዎች በመጣስ የመጨረሻ ዉሳኔ መስጠታቸዉ በግልጽ ሲረጋገጥ፤ በተጨማሪም በአንድ ማስረጃ ይዘት ላይ በግልጽ የተመለከተዉን ወይም በምስክሮች ተመስክሮ የተረጋገጠዉን በአግባቡ ያላገናዘበ እና ዉሳኔ የሚሻዉ የፍሬ ነገር ጭብጥ መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ አስፈላጊ ለሆነ ማስረጃ ተገቢዉን ዋጋ ሳይሰጡ ዉሳኔ መስጠት እንዲሁም በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠዉን ነጥብ ከሕጉ ጋር ሳያገናዝቡ መወሰን ማስረጃ ወደ መመዘን ዉስጥ ተገብቷል የሚያስብል ሳይሆን እንደመሰረታዊ የሕግ ስህተት ተቆጥሮ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚገባ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መሆኑን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት  ከዚህ ጋር በተያያዘ በሰ/መ/ቁጥር 45595፣64813 (በቅጽ 12 የታተሙ)፣89676(በቅጽ 17 የታተመ)፤ 225975 (ያልታተመ)፤228017(ያልታተመ)እና በሌሎች መዛግብት ላይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

ፍርድ ቤቶችም ክርክር ሲሰሙ፣ማስረጃ ሲመረምሩና ሲመዝኑ እንዲሁም ዳኝነት በተጠየቀበት ጉዳይ ላይ ዉሳኔ ሲሰጡ ከማንኛዉም ተጽዕኖ ነጻ በመሆን ከሕግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ ሳይመሩ የወንጀል ሕጉን ግብ፣ ዓላማዎችና መርሆዎች ባከበረ እንዲሁም የተጎጂዉን እና የከሳሹን መብቶች ማዕከል ባደረገ አኳኋን የቀረበላቸዉን ክስ፣ክርክርና ማስረጃ በአግባቡ አግባብነት ካለዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር አገናዝበዉ በመመርመር በገለልተኛነት እና በሙሉ ነጻነት የዳኝነት ተግባራቸዉን የማከናወን ግዴታ እና ኃላፊነት እንዳለባቸዉ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 9(1፣2፣ እና 4)፣13፣20 37፣79(2 እና 3)፣ከዋናው የወንጀል ሕጉ ክፍል እና ከወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕጉ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ የፍ/ቤቶች በግራ ቀኙ ተከራካሪዎች የቀረቡትን ማስረጃዎች የመስማትና የመመርመር ዋናዉ ዓላማም እዉነትን በፍሬ ነገር ደረጃ ማረጋገጥ ነዉ፡፡

በተያዘው ጉዳይ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 285713 በሆነ መዝገብ አመልካች በተከሰሰበት ድንጋጌ ስር ይከላከል ከተባለ በኃላ በቀን 16/12/2014ዓ.ም በዋለው ችሎት አመልካች የተከሳሽነት ቃሉ ከሰጠ በኃላ ሶስት መከላከያ ምስክሮች (1ኛ መከላከያ ምስክር ግሩም ታምራት፤

2ኛ መከላከያ ምስክር አስማማው መዝሙር፤ ሶስተኛ መከላከያ ምስክር ይልቃል ማሞ፤ እና አራተኛ መከላከያ ምስክር ምክትል ሳጅን እውነቱ ደሳለው የተባሉ) ቀርበው የተሰሙ ሲሆን፤ ቀሪ አንድ መከላከያ ምስክር ዶ/ር ሲሳይ ደመቀ የተባሉ በ3/2/2015ዓ.ም ቀርበው መሰማታቸው አጠቃላይ አመልካች የተከሳሽነት ቃሉ ከሰጠ በኃላ አምስት መከላከያ ምስክሮች ማሰማቱ ከስር መዝገብ ለመመልከት ተችሏል፡፡ ተጠሪ ለሰበር አቤቱታው በሰጠው መልስም አመልካች የተከሳሽነት ቃሉ በመስጠት አምስት መከላከያ ምስክሮች ማሰማቱ ያምናል፡፡ ሆኖም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩ መርምሮ ጥር 4 ቀን 2015ዓ.ም ፍርድ ሲሰጥ በፍርድ ሀተታው ላይ አመልካች አንድ መከላከያ ምስክር ማሰማቱን ጠቅሶ ባሰማው አንድ መከላከያ ምስክርም ሆነ በፍርድ ቤት ትእዛዝ ባቀረባቸው ሰነድ ማስረጃዎች በተጠሪ የቀረበበትን ክስና ማስረጃ የሚያስተባብሉ እንዳልሆኑ ጠቅሶ አመልካች በተከሰሰበት ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ ነው በማለት ፍርድ መስጠቱን ያሳያል፡፡

ከዚህም መረዳት የሚቻለው የአመልካች የተከሳሽነት ቃሉ በመስጠት አምስት መከላከያ ምስክሮች አሰምቶ እያለ አንድ መከላከያ ምስክር ብቻ እንዳቀረበ ተቆጥሮ ውሳኔ መሰጠቱ የማስረጃ ምዘናን መሰረታዊ መርሆዎች በመጣስ የተሰጠ ፍርድ መሆኑን የሚያሳይ ነው በህግ የተዘረጋውን የማስረጃ ምዘና መርህን ባልጠበቀ መልኩ የሚሰጥ ዳኝነት የግልጽነት መርህን የሚቃረንና ውጤቱም የተከራካሪ ወገን መሰረታዊም ሆነ ስነስርኣታዊ መብት የሚጎዳ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱም ቢሆን በመ/ቁ 242076 በሆነ መዝገብ ግንቦት 11 ቀን 2015ዓ.ም ሲወስን አመልካች በይግባኝ ደረጃ ካቀረባቸው ቅሬታ ነጥቦች አንዱ የሰጠሁት የተከሳሽነት ቃልና አራት መከላከያ ምስክሮቼ ቀርበው የሰጡት የምስክርት ቃል በፍርዱ ሳያካትት መወሰኑ ተገቢነት የለውም የሚል ሆኖ ሳለ ይህንኑ የአመልካች ቅሬታ መሰረት በማድረግ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች የሰጠው የተከሳሽነት ቃል እንዲሁም ያሳማቸው አምስት መከላከያ ምስክሮች የሰጡት የመከላከያ ምስክርነት ቃል መሰረት በማድረግ ማስረጃው በተሟላ ሁኔታ መዝኖ እንዲወስን መመለስ ሲገባው በአመልካች በኩል ባሰማው አንድ መከላከያ ምስክር እና የሰነድ ማስረጃዎች አልተከላከለም በማለት በአመልካች ላይ የተወሰነውን የጥፋተኝነት ውሳኔ ማጽናቱ የማስረጃ ምዘና መርህን በጠበቀ መልኩ መወሰናቸው የሚያሳይ ባለመሆኑ ጉዳዩ ወደ ስር ፍርድ ቤት ተመልሶ በአመልካች በኩል የሰጠው የተከሳሽነት ቃልና ቀርበው የተሰሙት አምስት መከላከያ ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ቃል ባካተተ መልኩ ጉዳዩን መርምሮ የመሰለውን ሊወስን የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ሲጠቃለል የስር ፍርድ ቤቶች በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4)ሸ እና 10(1)(ለ) ስር ከተመለከተው መመዘኛ አንጻር መሰረታዊ የህግ ስህተት የፈፀሙ በመሆኑ ታርሞ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፈደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 285713፤ ጥር 04 ቀን 2015 ዓ.ም በአመልካች ላይ ያስተላለፈው የጥፋተኝነት ውሳኔም ሆነ ጥር 18 ቀን 2015ዓ.ም ያስተላለፈው የቅጣት ውሳኔ እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 242076፤ በቀን11/9/2015ዓ.ም የጥፋተኝነት ውሳኔ በማጽናት የቅጣት ውሳኔው በማሻሻል የሰጠው ውሳኔ በፌዴራል ጠቀላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት የስር ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ በአመልካች በኩል የሰጠው የተከሳሽነት ቃል እንዲሁም ቀርበው የተሰሙት አራት መከላከያ ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ቃል ባካተተ መልኩ ተገቢውን የማስረጃ ምዘና መርህ በጠበቀ መልኩ ማስረጃ መዝኖ ህግን መሰረት በማድረግ እንዲወስን ተመልሶለታል፡፡
3. በውሳኔው መሰረት ለመፈጸም ያስችለው ዘንድ የውሳኔው ትክክለኛ ግልባጭ ለስር ፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይድረሰው ብለናል፡፡
4. በዚህ ሰበር ክርክር ምክንያት የወጣ ወጪ ቢኖር ግራቀኙ ይቻቻሉ፡፡ የስር መዝገብ በመጣበት ሁኔታ ተመላሽ ይደረግ ተብሏል፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

የሰ/መ/ቁ -247777

ጥቅምት 05 ቀን 2017

**ዳኞች**፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

ሰናይት አድነው

ሀፊዝ አባጀማል

**አመልካች**፡- አቶ አዳም ተክሌ ጉራሮ ጠበቃ ነብይ ተፈራ

**ተጠሪዎች**፡- 1. ወ/ሮ ፅጌ በሬሳ ቀርቧል

2. የአዲስ ከ/ክ/ከተማ ወረዳ 9 ቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

<u>**ፍ ር ድ**</u>

ይህ ጉዳይ የተጀመረዉ በአዲስ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን፣ አመልካች በተጠሪዎች ላይ ባቀረበዉ ክስ ሟች ወ/ሮ ሞቱ ጉራሮ ከህፃንነቴ ጀምሮ ከወላጆቼ በመውሰድ በአዲስ ክ/ከተማ ወረዳ 9 የቤት ቁጥር 742 በሆነው ቤት ውስጥ ያሳደጉኝ ሲሆን ሟችን እንደ እናቴ እያየሁ እስከ እለተሞታቸው ድረስ እየተንከባከብኳቸው በቤቱ ባዶ ቦታ ላይ ቤት ላይ በሰራሁት ቤት ውስጥ አግብቼ ልጆች ወልጄ እየኖርኩ ነው፡፡ ወ/ሮ ሞቱ ጉራሮ ሰኔ 2 ቀን 2012 በሞት የተለዩ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ ቤቱን ለቃ የወጣችና ትዳር መስርታ ልጆች ወልዳ እየኖረች በአራዳ ክ/ከተማ ወረዳ ልዩ ስሙ ዩሐንስ ተብሎ በሚጠራ አካባቢ በራሷ ስም የግል ቤት ሰርታ ስትኖር ወ/ሮ ሞቱ ሲታመሙ ሊሞቱ ይችላሉ በማለት በግሏ የነበረውን ቤት ወደ ልጇ ስም በማዞር ሟች ከሞቱም በኃላ ህግና መመሪያ ከሚፈቅደው ውጭ ብቻዋን የቤት ኪራይ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ተዋውላለች፡፡ በመሆኑም አመልካች በአከራካሪው ቤት ውስጥ ከሟች ወ/ሮ ሞቱ ጉራሮ ጋር

እንደ እናት እያሳደጉኝ በመሆኑ እስከ አሁንም በዚህ ቤት ውስጥ እየኖርኩኝ በቤቱ ላይ መብት ያለኝ በመሆኑ 1ኛ ተጠሪ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ያደረጉት ውል አመልካችንም እንዲያካትት ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት የጠየቀዉን ዳኝነት መሠረት ያደረገ ነዉ፡፡

1ኛ ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መልስ ቤቱን ለቅቄ አልወጣሁም፤ አሁንም በቤቱ ውስጥ እየኖርኩ ነው፤ አመልካች ከሟች ያልተወለደ በመሆኑ እኔ የሟች ወ/ሮ ሞቱ ጉራሮ ልጅ እያለው ከአመልካች ጋር በጋራ ውል መዋዋል አለብኝ በማለት ያቀረበዉ ዳኝነት መመሪያ ቁጥር 5/2011 መሠረት ያደረገ አይደለም በማለት የአመልካች ክስ ውድቅ ይደረግለት ዘንድ ተከራክራለች፡፡ 2ኛ ተጠሪ ባቀረበዉ መልስ በመመሪያ 5/2011 አንቀጽ 16(1)ሐ የመንግስት ቤት የሚተላለፍላቸው ቅደም ተከተል መሰረት 1ኛ ተጠሪ የቀድሞ ቤቱ ተከራይ ልጅ መሆናቸውና ወረሽነት ማስረጃ በማቅረባቸው በመመሪያው መሰረት ከ2ኛ ተጠሪ ጋር 1ኛ ተጠሪ በመመሪያው መሰረት ውል ከማዋዋል ውጪ 2ኛ ተጠሪ አመልካችን በቤቱ ላይ ውል ማዋዋል የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት ስለሌለ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበውን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኂላ አመልካች ከልጅነቱ ጀምሮ በአከራካሪው ቤት ውስጥ ከሟች ወ/ሮ ሞቱ ጉራሮ ጋር እንደ ልጅ ያደገ እና በቤቱ ውስጥም ትዳር መስርቶ እየኖረበት ያለ ቤት በመሆኑ በመመሪያ 5/2011 አንቀጽ 16(1)ሐ መሰረት አመልካች በቤቱ ላይ የመኖር መብት ያለው በመሆኑ በቤቱ ላይ አመልካች ውል ሊዋዋል ይገባል፡፡ በሌላ በኩል 1ኛ ተጠሪ በራሳቸው ስም የግል ቤት የሌላቸው በመሆኑ እና በአከራካሪው ቤትም እየተመላለሱ ወላጅ እናታቸውን ሲረዱ እንደነበር ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ በቋሚነት በቤቱ ሲኖሩ እንደነበር በመረጋገጡ 2ኛ ተጠሪ መመሪያዉ በሚፈቅደው መሰረት ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ያደረጉት የቤት ኪራይ ውል ሊቋረጥ አይገባም፡፡ 2ኛ ተጠሪ እና 1ኛ ተጠሪ በአከራካሪው ቤት ቁጥር 742 ላይ ቤት ኪራይ ውል "እነ" በማለት አመልካችን በማካተት ውል ሊያዋዉላቸው ይገባል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪዎች በዚህ ዉሳኔ ባለመስማማት ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ ክርክር በተነሳበት ቤት ላይ የቀድሞ ኪራይ ውል የፈፀሙት ወ/ሮ ሞቱ ጉራሮ ሲሆኑ እሳቸው ሲሞቱ በመመሪያው አንቀጽ 16(1)(ለ) መሰረት የሟች ልጅ የሆኑት 1ኛ ተጠሪ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ውል ተዋውለዋል፡፡ ይህም በመመሪያው መሰረት ቅድሚያ ለሟች ልጆች ቤቱ ሊተላለፍ የሚገባ በመሆኑ ነው፡፡ አመልካች ውል የመዋዋል መብት ሊያገኙ ይችሉ የነበረውም የሟች ልጆች በሌሉ ጊዜ ከሟች ልጆች በመቀጠል ብቻ ነው እንጂ የሟች ልጆች እያሉ ውል መፈፀም እንደማይችሉ መመሪያው ያመለክታል፡፡ በዚህ መሰረት ሟች ወ/ሮ ሞቱ ጉራሮ ከዚህ አለም በሞት ሲለዩ የመከራየት መብት የሚተላለፈው ለሟች ህጋዊ ባል፣ ልጅ እና እንደ ልጅ ላደጉ እንደ ቅደም ተከተላቸው በመሆኑ አመልካች የሟች ልጅ እያሉ ቤቱን እንዲከራዩ የሚያስችላቸው ምንም አይነት መብት የለም፡፡ አመልካች ተከራይነት መብት እንዳያገኙ ያደረጋቸው ለክርክር መነሻ በሆነው ቤት ውስጥ እንደ ልጅ አለማደጋቸው ሳይሆን መመሪያው የኪራይ መብት የሚፈጠረው ባስቀመጠው ቅደም ተከተል መሰረት መወሰን ሲገባው አመልካች እንደ ልጅ ያደጉ መሆናቸው ያልተካደ በመሆኑ ቤቱ ላይ የመከራየት መብታቸውን የማያስቀር ስለሆነ በቤቱ ላይ ውል ከተዋዋሉት 1ኛ ተጠሪ ጋር እነ በሚል ውል ሊዋዋሉ ይገባል ሲል የደረሰበት መደምደሚያ የመመሪያን የህግ ድንጋጌ እና የቀረበለትን ማስረጃ ባላገናዘበ መልኩ የሰጠው ውሳኔ ነው በማለት አመልካች አከራካሪ በሆነው የመንግስት ቤት ላይ እነ ተብሎ የኪራይ ውል ሊዋዋል አይገባም በማለት የስር ፍ/ቤት ውሳኔ በማሻሻል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ዉሳኔ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ባለመስማማት ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን፣ ሰበር ሰሚዉ ችሎት የቀረበውን የሰበር አቤቱታ አያስቀርብም በማለት ሰርዞታል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም ይህንኑ ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካች ግንቦት 23 ቀን 2015 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በቀረበ 04 ገጽ የሰበር አቤቱታ የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎት መመሪያ ቁጥር 5/2011 ላይ የተቀመጠውን የአጻጻፍ ቅደም ተከተል የመብት ቅደም ተከተል አድርገው በመውሰድ እንደ ልጅ ያደገ መብቱ የሚከበረው ልጅ ከሌለ ብቻ ነው በማለት የሰጡት ትርጉም መመሪያውን በግልጽ የሚሽር ነው፡፡ መመሪያው የተፈጥሮ ልጅ፣ እንደ ልጅ ያደገ በሚል ሲዘረዝር አንዱ ከሌለ የሌላው መብት ይጠበቃል ከሚል እሳቤ እንጂ የተፈጥሮ ልጅም እንደ ልጅ ያደገም አብረው አንድ የመንግስት ቤት ከኖሩ መብቱ የሚከበረው የተፈጥሮ ልጅ ብቻ ነው በማለት ትርጉም መስጠታቸው ያለግባብ ስለሆነ በአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት እና በአዲስ አበባ ከተማ  የይግባኝ  ሰሚ ሰበር ችሎት የተሰጠው ውሳኔዎች ተሽረው የአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ እንዲፀናልኝ የሚል ነው፡፡

የሰበር አቤቱታዉ ተመርምሮም አመልካች አከራካሪ በሆነው የመንግስት ቤት ላይ "እኔ" ተብለው የኪራይ ውል ሊዋዋሉ አይገባም ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ በአዲስ አበባ ከተማ የመንግስት ቤቶች አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 5/2011 የቀበሌ መኖሪያ ቤት የኪራይ ውል ለሶስተኛ ወገን ስለማስተላለፍ የተደነገገውን የተከተለ መሆን አለመሆኑን፤ እንዲሁም የወረዳው ቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት ስለሚኖረው የማረጋገጥ ኃላፊነት (administrative satisfaction) እና በመመሪያው ስለ አቤቱታ እና ቅሬታ አቀራረብ ስነ ስርዕት የተደነገገውን መሰረት በማድረግ የተወሰነ መሆን አለመሆን አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል ተብሏል፡፡ በዚህም መሠረት 1ኛ ተጠሪ ጥር 15 ቀን 2016 ዓ.ም አዘጋጅቶ ባቀረበ መልስ፤ በመመሪያ ቁጥር 5/2011 አንቀጽ 16(1)(ረ) ድንጋጌ መሰረት የቀበሌ ቤትን የተከራየ ማንኛውም ሰው በሞት ወይም አካባቢውን በተለያየ ምክንያት ሲለቅ በቤቱ ውስጥ ወይም ባል ወይም ሚስት ካሉ በቤቱ ላይ ውል የመዋዋል የመጀመሪያ መብት የሚኖራቸው እነርሱ በህይወት ከሌሉ ደግሞ የሚች ልጆች እና ጉዲፈቻ ልጆች በመኖሪያ ቤቱ ላይ ውል የመዋዋል የቅድሚያ መብት ያላቸው መሆኑን ከድንጋጌው መንፈስ መረዳት ይቻላል፡፡ 1ኛ ተጠሪ የቤቱ ዋና ተከራይ የነበሩት የወ/ሮ ሞቱ ጉራሮ ልጅ መሆኔን እንዲሁም አመልካች እንደ ልጅ ቤቱ ውስጥ ስለመኖሩ ራሱ በስር ፍ/ቤትም ሆነ በዚህ ችሎት ያመኑት ጉዳይ በመሆኑ የአዲስ አበባ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት እና ሰበር ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔ ከመመሪያ አኳያ የሚነቀፍ ምክንያት ስለሌለው የአመልካች አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግ በማለት ተከራክረዋል፡፡ 2ኛ የሰበር ተጠሪም በቀን ጥር 15 ቀን 2016 ዓ.ም አዘጋጅተው ባቀረቡት መልስ አመልካች ቅሬታቸውን በየደረጃው ለተቋቋመው የቅሬታ ሰሚ አካላት ባላቀረቡበት ይህንን ስለማድረጋቸው ማስረጃውን ባላቀረቡበት ሁኔታ ጉዳዩን ቀጥታ ለፍርድ ቤት ሊያቀርቡ አይችሉም፡፡ በአዲስ አበባ የመንግስት ቤቶች መመሪያ ቁጥር 5/2011 አንቀጽ 16 መሰረት ባስቀመጠው ደረጃ መሰረት ባል/ሚስት ካለ ለእነሱ እነሱ ከሌሉ ልጅ እና ጉዲፈቻ ልጅ እነሱም ከሌሉ ደግሞ የወረዳው አስተዳደር ሲያረጋግጥ እንደ ልጅ በቤቱ ውስጥ ለኖረ እንደቅደም ተከተላቸው ሊተላለፍ እንደሚችል መመሪያው ያስቀምጣል፡፡ በዚህ መሰረት 1ኛ ተጠሪ የቤቱ ተከራይ በሞቱ ጊዜ ልጅ ስለመሆናቸው የወራሽነት ማስረጃ በማቅረባቸው የቤቶች መመሪያ በሚያዘው መሰረት በቅደም ተከተል መሰረት የቤቱን ኪራይ ውል ያዋዋልን በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ በከተማዉ ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ስህተት የተፈጸመበት አይደለም የሚልባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር ፀንቶ እንዲወሰንለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ በመስጠት ተከራክሯል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት በአጭሩ ከላይ የተመለከተዉን ሲመስል ይህ ችሎትም መዝገቡን ለማስቀረብ የተያዘዉን ጭብጥ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረበዉ ክስ ለጠየቀዉ ዳኝነት መሠረት ያደረገዉ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት ተከራይ ከነበሩት ሟች ወ/ሮ ሞቱ ጉራሮ ዘንድ ከልጅነታቸዉ ጀምሮ አድገዉ በቤቱም ከሟች ጋር ሲኖሩ የነበሩ መሆኑንና በአንፃሩ ግን 1ኛ ተጠሪ የግል ቤት እያላቸዉ ከቅን ልቦና ዉጪ ሟች ሊሞቱ አካባቢ መጥተዉ በቤቱ ዉስጥ መኖር የጀመሩ እና የግል ቤታቸዉን ስመ ሀብት በልጃቸዉ ስም እንዲሆን ማድረጋቸዉን ሲሆን፣ የጠየቁት ዳኝነትም ከ1ኛ ተጠሪ ጋር "እነ" ተብሎ የኪራይ ዉሉን እንዲዋዋሉ እንዲወሰንላቸዉ ነዉ፡፡ የአመልካች መከራከሪያ አንድም የሟች ልጅ ባልሆንም በሟች ዘንድ ስላደግኩኝ የቤቱን ኪራይ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር የመጋራት መብት አለኝ የሚል ሲሆን፣ ሁለትም 1ኛ ተጠሪ የግል ቤት ስላላቸዉ መብት የላቸዉም የሚል ይዘት ያለዉ ነዉ፡፡ በመንግስት ቤቶች አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 5/2011 አንቀጽ 16(1) የቀበሌ ቤት ወደ ሦስተኛ ወገን ሊተላለፍ የሚችልበትን አግባብ የሚደነግግ ሲሆን፣ ቤቱ በኪራይ ለሦስተኛ ወገን የሚተላለፍበትንም ሁኔታ በቅደም ተከተል ያስቀምጣል፡፡ በዚህም መሠረት በመጀመሪያ ረድፍ ላይ የሚመጡት የሟች ልጆች ሲሆኑ ከዚህ ዉጪ ያሉት እና በመመሪያዉ መሠረት ቤቱን የመከራየት መብት ያላቸዉ ሰዎች ከዚህ በኋላ እንደየቅደም ተከተላቸዉ በመብቱ ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ከመመሪያዉ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህም ማለት ከሟች ልጆች ዉጪ ያሉት ሌሎች ሰዎች የመከራየት መብት የሚያገኙት የኪራይ መብቱ ሊተላለፍለት የሚገባ የሟች ልጅ የሌለ ሲሆን ብቻ በመሆኑ፣ የሟች ልጅ ያልሆኑ ሌሎች ሰዎች ከሟች ልጅ ጋር በጋራ "እነ" በሚል የኪራይ ዉል እንዲደረግ መጠየቅ አይችልም፡፡ በመሆኑም 1ኛ ተጠሪ ቤቱን የመከራየት መብት አላቸዉ ቢባል እንኳን የኪራይ ዉሉ በሁለታችን ሊሆን ይገባል በማለት አመልካች የሚያቀርበዉ ክርክር ከፍ ሲል የተመለከተዉን የመመሪያዉን ትክክለኛ ይዘት ያገናዘበ ባለመሆኑ ተቀባይነት ያለዉ አይደለም፡፡

በሌላ በኩል ከላይ እንደተመለከተዉ የአመልካች አንዱ መከራከሪያ 1ኛ ተጠሪ የግል ቤታቸዉን ከቅን ልቦና ዉጪ በስማቸዉ አድርገዋል የሚል ነዉ፡፡ በርግጥ የመንግስት ቤቶችን የመኖሪያ ቤት ኪራይ ዓይነተኛ ዓላማ የመኖሪያ ቤት ለሌላቸዉ ሰዎች በዝቅተኛ የኪራይ ዋጋ የመኖሪያ ቤት ተጠቃሚ ማድረግ እንደሆነ ይታመናል፡፡ በመሆኑም 1ኛ ተጠሪ የግል የመኖሪያ ቤት ያላቸዉ መሆኑ ከተረጋገጠ ቤቱን የኪራይ መብት ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉበት የህግ አግባብ የለም፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበዉን ክርክር ዉድቅ ያደረገዉ በ1ኛ ተጠሪ ስም የተመዘገበ የመኖሪያ ቤት አለመኖሩን ጠቅሶ የአራዳ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ምላሽ የሰጠዉ መሆኑን በመጥቀስ ነዉ፡፡ ይሁንና፣ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰዉ፣ አመልካች የሚከራከረዉ 1ኛ ተጠሪ የቤቱን ስመ ሀብት በልጃቸው ስም ያደረጉ መሆኑን ነዉ፡፡ ፍርድ ቤት የግራ ቀኝ ክርክር መሠረት ያደረገ እና ለጉዳዩ ትክክለኛ ዉሳኔ ለመስጠት የሚያስችል ጭብጥ መያዝ እንዳለባቸዉ በፍትሐብሔር ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 246(1)፣ 247(1) እና 248 ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም በተያዘዉ ጉዳይ ላይ ከአመልካች ክርክር አኳያ ፍትሐዊ ዉሳኔ ለመስጠት መያዝ የሚገባዉ ትክክለኛ ጭብጥ፣ በ1ኛ ተጠሪ ስም የተመዘገበ ቤት መኖር አለመኖሩን ብቻ ሳይሆን፣

አመልካች እንደሚለዉ 1ኛ ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ በሆነዉ የኪራይ መብት ተጠቃሚ ለመሆን በማሰብ የግላቸዉን ቤት ስመ ሀብቱ በልጃቸዉ ስም አድርገዋል ወይ? የሚል ነዉ፡፡ በዚህ ጭብጥ መሠረት አጣርቶ በተገቢዉ የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ይቻል ዘንድም አመልካች የራሳቸዉን ቤት በልጃቸዉ ስም አድርገዋል? አላደረጉም? በልጃቸዉ ስም አድርገዉ ከሆነ በምን ምክንያት በልጃቸዉ ስም አደረጉ? በልጃቸዉ ስም የተመዘገበዉ መቼ ነዉ? የሚሉትን ጭብጦች በተጓዳኝነት በመያዝ መመርመር ያስፈልጋል፡፡

ይሁንና የስር ሁለቱም ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ከዚህ አኳያ አልመረመሩትም፡፡ በመሆኑም በጉዳዩ ላይ ፍትሐዊ ዉሳኔ ለመስጠት የሚያስችላቸዉን ትክክለኛ ጭብጥ በመያዝ 1ኛ ተጠሪ ቤቱን የመከራየት መብት ያላቸዉ መሆን አለመሆኑን መርምረዉ ዉሳኔ ሰጥተዋል ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ በዚህም ምክንያት የስር ሁለቱም ፍርድ ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይሁንና ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ ፍርድ ቤት በዚህ አግባብ ባያጣራም አመልካች በጠየቀዉ ዳኝነት መሠረት የኪራይ ዉሉን ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በጋራ እንዲዋዋሉ ተወስኖለታል፤ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ያቀረቡትም ተጠሪዎች ናቸዉ፡፡ በመሆኑም 1ኛ ተጠሪ ቤቱን የመከራየት መብት የላቸዉም ከተባለም ዉጤቱ አመልካች በግማሹ ላይም ቢሆን መብት ያለዉ መሆን አለመሆኑን ለመወሰን እንዲቻል እንጂ 1ኛ ተጠሪ ጉዳዩን በመጀመሪያ በተመለከተዉ ፍርድ ቤት በሰጠዉ ፍርድ መሠረት ያገኙትን መብት እንዲያጡ የማድረግ ዉጤት ሊያስከትል አይገባም፡፡ ይህንኑ ታሳቢ በማድረግም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ዉሳኔ</u>**

1. የአዲስ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 40131 ላይ ሚያዝያ 17 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ እንዲሁም የከተማዉ አስተዳደር ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 41094 ላይ ግንቦት 15 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ትዕዛዝ በሰበር ሥ/ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ተዘግቶ የነበረዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ ከላይ በፍርድ ክፍል የተመለከቱትን ጭብጦች መሰረት በማድረግ የግራ ቀኝን ክርክር እና ማስረጃ እንዲሁም እንዳግባብነቱ ተጨማሪ ማስረጃዎችን በማስቀረብ ጭምር አጣርቶ ተገቢዉን እንዲወስን ጉዳዩ በሰበር ሥ/ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(2) መሠረት ተመልሶለታል፡፡
3. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
4. የሰበር አጣሪ ችሎት ግንቦት 29 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ እግድ ተነስቷል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ/ጋ

<u>ማስታወሻ</u>፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የሰ/መ/ቁ 248002

ጥቅምት 05 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ብርሃኑ መንግስቱ

ማርታ ተካ

አመልካች፡-1.አቶ ጎብሌ ሀርቤ ---- ቀረቡ

2 አቶ ፌቴራ ሀረቤ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ዳንጊቴ ዳዋሳ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ጉዳዩ የገጠር እርሻ መሬት ለመረከብ የቀረበ ክርክር ሲሆን የተጀመረው የሲዳማ ክልል የቡርሳ ወረዳ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች ተከሳሾች የአሁን ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ በመሆን እንዲሁም የሰበር ክርክር አካል ያልሆኑ አቶ ሀንቃሎ ሀረቤ ጣልቃ ገብ ሆነው ተከራክረዋል፡፡

ለሰበር መቅረብ ምክንያት የሆነው የአሁኖቹ አመልካቾች የቡርሳ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 13444 በቀን 18/08/2014 ዓ.ም አመልካቾች በጉልበት የወሰዱት መሬት የለም በማለት ክሱን ውድቅ በማድረግ የወሰነውን ፣የበንሳ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 05242 በቀን 06/12/2014 ዓ.ም የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ምክንያቱን በመቀየር በማጽናት የሰጠውን ውሳኔ የሲዳማ ክልል ጠቅላይ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ፍርድ ቤት በመ/ቁ 04132 በቀን 18/04/2015 ዓ.ም አመልካቾች ድንበር አልፈው የሰሩትን ቤት አፍርሰው ያንሱ በማለት በስሩ ያሉት ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔን በመሻር መወሰኑ እንዲሁም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 04896 በቀን 30/072015 ዓ.ም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ ማረም ሲገባው ማጽናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በሚል እንዲታረምላቸው በመጠየቃቸው ነው ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ፡- የአሁን ተጠሪ ከሳሽ በመሆን በአሁኑ አመልካቾች ላይ ያቀረቡት ክስ ይዘቱ ሲታይ ፡- አመልካቾች የእኔ ጣውንት/ሁለተኛ ሚስት/ ልጆች ሲሆኑ የእኔ ባለቤት የሆነው አባታቸው ሟች አቶ ሀርቤ ዋርቶ ከዚህ አለም በሞት ሲለይ አመልካቾች አንቺ ሴት ልጆች ስለወለድሽ መሬቱ ለአንችም ሆነ ለልጆችሽ አይመለከትም ሀሮና ቡሌ ቀበሌ ልዩ ቦታ ዳራሬ ላንጎ ሴል ውስጥ የሚገኙ በሁለት ቦታ የሚገኙ በክስ ማመልከቻ ውስጥ አዋሳኞች የተጠቀሱት መሬቶች በላያቸው ላይ ቀርካ ፣እንሰት፣ በቃርካ የተሰራ ቤትና ጥድ ያለበትን ቤትም ሆነ አጥር አፍርሰው የወሰዱብኝ በመሆኑ በጉልበት በያዙብኝ መሬት አመልካቾች ለቀው እንዲወጡ ይወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

አመልካቾችም በስር ፍርድ ቤት ተከሳሾች ሆነው የሰጡት መልስ ተጠሪ በክስ ማመልከቻቸው ላይ አዋሳኞን የጠቀሱዋቸው መሬቶች ሀለቱም የተጠሪ መሬት እንዳልሆኑ፣ 1ኛው መሬት የ1ኛው አመልካች እናት ወ/ሮ ሹሩ ዳንባራ እና 2ኛ አመልካች እናት ወ/ሮ ላሎ ቃንቁራ የአባታቸው አቶ ሀርቤ ዋርቶ ሚስቶች ሆነው ከአባታችን ድርሻቸውን አግኝተው ይዘው የቆዩት መሬት ሲሆን ከእናትና ከአባታችን በውርስ የተላለፈልን ነው 2ኛው መሬት 1ኛ አመልካች አባት እና እናት በህይወት በነበሩበት ጊዜ አባቴ ሰጥቶኝ ለ28 ዓመታት በላይ እየተጠቀምኩ የምገኝ መሬት በመሆኑ ለተጠሪ ለቀን ልናስረክብ አይገባም የሚል ነው፡፡

እንዲሁም ስር ጣልቃ ገብ በፍ/ብ/ስ/ስ ህግ ቁጥር 41 መሰረት ወደ ክርክር የገቡ ሲሆን ግራ ቀኙ እያተከራከሩበት ያለው መሬት የአባቴ በመሆኑ እና ወራሽነት ያረጋገጥኩ በመሆኑ የሟች አባቴ ድርሻ ሊሰጠኝ ይገባል፡፡ እንዲሁም ሟች አባቴ ለኔ ሰጥቶኝ የነበረ በመሆኑ ለኔ ሊሰጠኝ ይገባል በማለት ጠይቀዋል፡፡

በጣልቃ ገብ አቤቱታ ላይ የአሁኗ ተጠሪ የሰጡት መልስ ለጣልቃ ገብ የተሰጠ መሬት የለም የሚል ሲሆን በአመልካቾች በኩል ደግሞ ጣልቃገብ እንዲሰጣት የጠየቀችው መሬት አባታችን አስቀድሞ የሰጣትን ነው በሚል ጣልቃገብን ክርክር በመደገፍ ተከራክረዋል፡፡

የስር ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና የሰው ምስክር በመስማትና ክርክር የተነሳበት መሬት ጉዳዩን የሚያውቁ በአካባቢ ሽማግሌዎች የምስክርነት ቃላቸውን በማስማት እንዲሁም ፍርድ ቤቱ በራሱ መሪ ማጣራት ማድረጉን ጠቅሶ በመ/ቁ 13444፤ ማያዝያ 18 ቀን 2014 ዓ/ም ሲወስን፡-

በቡርሳ ወረዳ ሀሮር ቡሌ ቀበሌ ልዩ ቦታ ዳራ ላግጎ ተብሎ በሚጠራበት የሚገኝ የታችኛው መሬት አቀማመጡ ከላይ መንገድ ፤ ከታች ረግረጋማ ውሃ በስተግራ አቶ እሞ ፍቼ፤ በስተቀኝ አቶ እላም ፍቼ ተከቦ የሚገኝ ያለውን ወደ ታች ሲቆም በቀኝ በኩል ጫፍ ከግማሽ ወደ ታች ወይም /የተጠሪ እንሰት ከሆነው ወደ ታች/ በመሀል የባህርዛፍ ድንበር ካለበት እስከታች ሬግረግ ውሃ ድረስ ያለ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

መሬትን አመልካቾች በጉልበት የወሰዱት ሳይሆን አባታቸው በህይወት እያሉ ድርሻቸው አድርገው የሰጡዋቸው መሬት መሆኑን፤ ተጠሪ በክስ ማመልከታቸው በአራቱ አቅጣጫ አዋሳን ጠቅሰው ከሚከራከሩበት መሬት ውስጥ የግራ ጎን ጫፍ ከተጠሪ አጥር ተነስቶ ከላይ እስከ ታች ድረስ ያለው መሬት ስር ጣልቃገብ አባታቸው በህይወት እያሉ የአካበቢ ሰዎች ጠርተው ተጠሪም ባሉበት ለስር ጣልቃገብ ድርሻ በማድረግ የሰጡት መሬት መሆኑን ስር ጣልቃገብ በምስክሮቹ ያስረዳና ፍርድ ቤቱም በመስክ ምልከታ ባደረገው ማጣራት ይህንኑ ለማረጋገጥ የቻለ በመሆኑ ይህ መሬት የስር ጣልቃገብ ነው፤ በዚሁ ቀበሌና ቦታ የላይኛው መሬት አቀማመጡን በክስ ማመልከቻ ተራቁጥር 2 ስር የተጠቀሰው መሬት 2ኛ አመልካች ተጠሪ የአባቱ ሚስት ሆነው ከመምጣታቸው በፊት አባቱ ከወላጅ እናቱ ጋር በትዳር እያሉ አባቱ ለ2ኛ አመልካች የሰጡት መሬት መሆኑና አባቱ ከመሞታቸው አስቀድሞ መሬቱ ይዞ ሲጠቀምበት የቆየ መሬት እንጂ በጉልበት የያዘው መሬት ባለመሆኑ ለተጠሪ ሊለቅ አይገባም በአጠቃላይ በአካባቢው ሽማግሎዎች ያለልዩነት በሰጡት የምስክርነት ቃልና ፍርድ ቤቱ በመስክ ምልከታ ባደረገው ማጣራት አመልካቾች በጉልበት የወሰዱት መሬት ባለመኖሩ ለተጠሪ የሚመልሱት መሬት የለም በሚል ወስኗል፡፡

የአሁኗ ተጠሪ በዚሁ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለበንሳ አከባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ግራቀኙን በጉዳዩ ላይ በማከራከርና ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ ተጨማሪ ማጣራት ካደገ በኋላ በመ/ቁ 05295 በቀን 06/12/2014 ዓ.ም ሲወስን፡- የስር ጣልቀገብ ድርሻ ነው ተብሎ በስር ተወሰነውን የውሳኔ ክፍል ሲሽር፤ አመልካቾችን በተመለከተ ግን በክስ ማመልካቻው ላይ 1ኛው መሬት ተጠሪ ከሶስት ዓመት በፊት የልጆቹ አባት ከሞቱ ወዲህ ሽማግሌዎችን በተገኙበት ለአመልካቾች ድርሻቸውን ለይተው መስጠታቸውንና አመልካቾችም በተሰጣቸው መሬት ላይ ቤት የገነቡበት መሆኑን በተደረገው ማጣራት ሊረጋገጥ መቻሉን፤ እንዲሁም 3ኛው መሬት 2ኛ አመልካች አባቱ በህይወት እያለ ጀምሮ ይዞ እየተጠቀመበት የቆየ መሬት እንጂ አመልካቾች በጉልበት እንዳልየዙ የተረጋገጠ

በመሆኑ የአሁኖቹ አመልካቾች ክስ የቀረበበት ይዞታ ለተጠሪ ሊያስረክቡ አይገባም በማለት በውጤት ደረጃ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

በመቀጠል የአሁኗ ተጠሪ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን በጉዳዩ ላይ በማከራከር በመ/ቁ 04132 በቀን 18/04/2015 ዓ/ም በስሩ ያሉ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ በመሻር ሊወስን የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ አመልካቾች ከአባታችን ሞት ከ3 ዓመት በኋላ ክርክር ያስነሳው መሬት ተጠሪ ሽማግሌ በተገኙበት ድርሻችን በመስጠት ተካፍለናል በሚል በስር መልሳቸው ያስነሳው መሬት ተጠሪ ሽማግሌ በተገኙበት ድርሻችን በመስጠት ተካፍለናል በሚል በስር መልሳቸው ባልተከራከሩበት ሁኔታ ከጭብጥ ውጪ በመውጣት ተጠሪ ሽማግሌዎች ጠርተው ለአመልካቾች ድርሻቸውን ማካፈላቸው ተረጋግጧል በሚል መወሰኑ አግባብ እንዳልሆነ፤ እንዲሁም አመልካቾች የያዙት መሬት በውርስ ያገኙት ስለመሆኑ ስላልተረጋገጠ አመልካቾች የሰሩት ቤትም ሆነ አጥር አፍርሰው የያዙት መሬት ለቀው ለተጠሪ ሊያስረክቡ ይገባል በማት ወስኗል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አመልካቾች የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በጉዳዩ ላይ ግራቀኙን ካከራከረ በኃላ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማጽናት በመ/ቁ 04896 በቀን 30/07/2015 ዓ.ም ወስኗል።

አመልካቾች በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ይታረምልን በማለት በቀን 28/09/2015 ዓ/ም ጽፈው ያቀረቡት አቤቱታ ይዘቱ ሲታይ ተጠሪ እና ከአመልካቾች አባት ጋር የተጋቡት በ1995 ዓ.ም ሲሆን 1ኛ አመልካች አባታችን ተጠሪን ከማግባቱ በፊት በጎጀ መውጫነት በ1983 2ኛ መሬት ተሰጥቶኝ የያዝኩት እንጂ ገፍቼ የያዝኩት ይዞታ አለመኖሩ በስር ፍርድ ቤቶች ተረጋግጦ እያለ፤ ይህንኑ ይዞታ ለ32 ዓመታት ባላዩ ላይ ንብረት አፍርቼ የምገለገልበት መሬቱ በአባቴ እና እናቴ በ1998 በጎጆ መውጫ የተሰጠኝ መሆኑ ተረጋግጦ የስር ወረዳውና ከፍተኛ ፍርድ ቤት በገለልተኛ ሽማግሌዎች ጉዳዩ እንዲጣራ በማድረግና እስከ ቦታው ድረስ በመሄድ ማጣራት አድርገው የውሰኑትን፤ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና ሰበር ሰሚ ችሎት ይህንኑ ውሳኔ መሻራቸው አግባብ እንዳልሆነ፤ በስር ፍርድ ቤት ይዞታውን ከወላጆቻችን እጅ ያገኘነው መሆኑን ገልፀን ተከራክረናል ነገር ግን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካቾች ከማን እጅና መቼ እንዳገኙ ገልጸው አልተከራከሩም በሚል መወሰኑ አግባብ ባለመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ይህን ሳያጣሩ ቤት አፋርሰን ድንበርዋን አልፈን መብቷን እንደተጋፋን አድርገው የሰጡት ውሳኔ የማስረጃ ምዘና መርህ የጣሰ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ውሳኔው ታርሞ የስር ወረዳውና ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲፀናልን በማለት አቤቱታ አቅርቧል።

ይህ በሰበር ሰሚ ችሎትም አመልካቾች አቤቱታ መርምሮ፡- በክልሉ ወረዳ ፍርድ ቤት በአካል ወደ ቦታው በመሄድ በአካባቢው በሽማግሌዎች ባደረገው ማጣራት ክርክር ያስነሳው መሬት በሟች አቶ ሀርቤ ዋርቶ ስም የተመዘገበ መሆኑን አመልካች እና ስር 2ኛ ተከሳሽ ከአባታቸው ያገኙት መሬት ሆኖ ቤት ገንበተው የሚኖሩት እንጅ ከተጠሪ በሀይልም ሆነ በጉልበት የያዙት አለመሆኑን በተረጋገጠበት እንዲሁም በክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በወረዳው ፍርድ ቤት ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር በተጨማሪ በጎረቤት ሽማግሌዎች በተገኙበት አመልካቾች የያዙት ይዞታ የራሳቸው እንዲሆን ተጠሪ ስምምነት መድረጓ ተረጋግጦ የተጠሪን ክስ ውድቅ በማድረግ የወሰነበትን፤ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካቾች በተጠሪ መሬት ላይ የገነቡት ቤት አፍርሰው መሬቱ ለተጠሪ

ሊያስረክቡ ይገባል በሚል የመወሰኑን አግባብነት በሰ/መ/ቁ 44804፤229926፤229475 እና በሌሎች መዝገቦች ላይ ከማስረጃ ምዘና መርሆች አተገባበር በሚመለከት ከተሰጡት ውሳኔዎች አንጻር ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል።

ተጠሪም በቀን 23/07/2016ዓ/ም የተጻፈ መልስ አቅርበዋል። በመልሳቸውም የተሰጠው ውሳኔ ከፍትሐብሔር ህግና ከመሬት ይዞታ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 110/99 አተገባበር አንጻር ሕጋዊና ፍትሀዊ ውሳኔ በመሆኑ ወጪና ኪሳራ የመጠየቅ መብት ተጠብቆልኝ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና ሰበር ሰሚ ውሳኔ ችሎት ይጽናልኝ በማለት መልስ ሰጥቷል። አመልካቾችም በቀን 16/08/2016ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል።

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን የተያዘው ጭብጥ ከግምት በማስገባት በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በተሰጠው ውሳኔ ላይ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል መሰረታዊ የሕግ ስህተት መፈጸም አለመፈጸሙን አግባብነት ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 80(1/ሀ) እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10(1/ሐ እና መ) መሰረት በክልል ፍርድ ቤቶች ታይቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠውን የመጨረሻ ውሳኔ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር ችሎት መመርመር የሚችለው በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሀ፣ለ እና ሸ) ስር መሰረታዊ የሕግ ስህተቶች ናቸው በሚል ከተደነገጉት መመዘኛዎች አንዱን ወይም ከአንድ በላይ የሆነ መመዘኛ የሚያሟላ ስህተት በመጨረሻ ውሳኔ ላይ ተፈጽሞ ሲገኝ ብቻ ነው፡፡በዚህ አግባብ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10(1/ሐ እና መ) ስር በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሊታረሙ የሚችሉ ስህተቶች በአዋጁ አንቀጽ 2(4/ሀ) ስር በተመለከተው መሰረት ሕገ መንግስታዊ ድንጋጌዎችን በሚቃረን አኳኋን በክልል ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ ሲሆን ፤በአዋጁ አንቀጽ 2(4/ሸ) ስር እንደተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ውሳኔ በሚቃረን አኳኋን በክልል ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ ሲሆን  በአንቀጽ 2(4/ለ) ላይ እንደተመለከተው ሕግን አላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው ድንጋጌ ተጠቅሶ የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ ሆኖ ይህ ውሳኔ የተሰጠበት ጉዳይ ለሕዝብ ጥቅም  ሀገራዊ ፋይዳ ያለው ጉዳይ በሚል በሕጉ ከተጠቀሱት ሦስቱ ምክንያቶች መካከል ቢያንስ አንዱን የሚያሟላ እና ፍትህ የሚያዛባ ጉልህ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት የመጨረሻ ውሳኔ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በተለያዩ መዛግብት ከሰጣቸው የሕግ ትርጉሞች መካከል አንዱ በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን እና በይግባኝ ሰሚነት የሚዳኙ ፍርድ ቤቶች የማሳረጃ አቀራረብን፣ አግባብነትን ፣ ተቀባይነትን እና ማስረጃ አቅርቦ አንድን ፍሬ ነገር የማሳረዳት ሸክም የሚመለከቱ መርሆዎች ( principles of production, relevancy ,admissibility and burden of proof of evidence) አተገባበር በሚቃረን አኳኋን እንዲሁም የማስረጃ ምዘናን ወይም የማስረዳት ደረጃን (standards  of proof of weight of evidence) የሚመለከቱ መሰረታዊ መርሆዎች በመጣስ የመጨረሻ ውሳኔ መስጠታቸው በግልጽ ሲያረጋግጥ እንደመሰረታዊ የሕግ ስህተት ተቆጥሮ በፌዴራልም ሆነ በክልል ሰበር ሰሚ ችሎቶች ታይቶ ሊታረም እንደሚችል ነው፡፡ እንዲሁም በአንድ ማስረጃ ይዘት ላይ በግልጽ የተመለከተውን በአግባቡ ያላገናዘበ ውሳኔ መስጠት ወይም በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠውን ነጥብ በሕጉ ጋር  ሳያገናዝቡ መወሰናቸው ከተረጋገጠ እነዚህን ስህተቶች በሰበር ችሎት ማረም ማስረጃ ወደ መመዘን ውስጥ ተገብቷል የሚያስብል ሳይሆን እንደመሰረታዊ  የህግ ስህተት ሊቆጠርና በሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን ማእቀፍ ውስጥ ታይቶ ሊታረም ይገባል ሲል ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 44804 (ቅጽ 11 ላይ እንደታተመው) 211615(ያልታተመ) 229926(ያልታተመ) እና በሌሎች መዛግብት ላይ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በሌላ በኩል ተጠቃሾቹ መርሆዎች መጣሳቸው እስካልተረጋገጠ ድረስ የቀረበውን ማስረጃ መርምረውና መዝነው አንድን አከራካሪ ፍሬ ነገር እንዲያረጋግጡ በህግ ስልጣን የተሰጣቸው ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ስልጣን እና በይግባኝ የሚዳኙ ፍርድ ቤቶች ማስረጃዎችን መርምረውን መዝነው የአከራካሪውን ፍሬ ነገር መኖር ወይም አለመኖር በማረጋገጠ የደረሱበትን የፍሬ ነገር ድምዳሜ ወደ ጎን በመተው ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ማስረጃ ወደመመርመርና መመዘን ጉዳይ ውስጥ በመግባት የአከራካሪውን ፍሬ ነገር መኖር ወይም አለመኖር ማረጋገጥ አይችልም፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ በኩል ክርክር ያስነሱት መሬቶች ከአመልካቾች አባት ጋር በጋራ ያገኙት ሆኖ እያለ አመልካቾች በጉልበት በመያዝ ቤትና አጥር መገንባታቸውን በመግለጽ የገነቡት ቤትም ሆነ አጥር በማፍረስ ለቀው ሊያስረክቡኝ ይገባል በሚል የሚከራከሩ ሲሆን በአመልካቾች በኩል ደግሞ በክስ ማመልከቻ ተራ ቁጥር 1 ስር የተጠቀሰው መሬት የ1ኛ አመልካች እናት ሹሬ ደንባራ እና የ2ኛ አመልካች እናት ወ/ሮ ላሎ ቃንቁራ ከአቶ ሀርቦ ዋርቶ የተከፈሉትን ድርሻ መሆኑን እና በውርስ የተላለፈላቸው መሆኑን እንዲሁም 2ኛ መሬት 1ኛ አመልካች አባታቸው ተጠሪን ከማግባታቸው በፊት ጀምረው መሬቱን ይዘው ለ28 ሲገለገሉበት የቆዩት መሬት መሆኑን በመግለጽ ነው፡፡ በዚህ መልኩ ግራ ቀኙ ካሰሙት ክርክር አንፃር ሊመሰረትና በተገቢው ማስረጃ ተረጋግጦ ሊወሰን የሚገባው ጭብጥ ተጠሪ በክስ ማመልከቻቸው የጠቀሱዋቸው የመሬት ይዞታዎች አመልካቾች በጉልበት ይዘዋል አልያዙም? የሚል ነው፡፡ በስር ወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ በግልጽ እንደተመለከተው በክስ ማመልከቻው ላይ በተራ ቁጥር 1 ስር የተመለከተው መሬት አመልካቾች በጉልበት የወሰዱት ሳይሆን አባታቸው በህይወት እያሉ ድርሻቸው አድርገው የሰጡዋቸው መሬት መሆኑን በክስ ማመልከቻ ተራ ቁጥር 2 ስር የተጠቀሰው መሬት 2ኛ አመልካች ተጠሪ የአባቱ ሚስት ሆነው ከመምጣታቸው በፊት አባቱ ከወላጅእናቱ ጋር በትዳር እያሉ በጎጆ መውጫነት የሰጡት መሬት መሆኑና አባቱ ከመሞታቸው አስቀድሞ መሬቱ ይዞ ሲጠቀምበት የቆየ መሬት እንጂ በጉልበት የያዘው መሬት አለመሆኑ በአጠቃላይ በአካባቢው ሽማግሌዎች ያለልዩነት በሰጡት የምስክርነት ቃልና ፍርድ ቤቱ በመስክ ምልከታ ባደረገው ማጣራት አመልካቾች በጉልበት የወሰዱት መሬት አለመኖሩ በማረጋገጥ ለተጠሪ የሚመልሱት መሬት የለም በሚል ወስኗል፡፡

የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ተጨማሪ ማጣራት ሲያደርግ በክስ ማመልከቻው ላይ 1ኛ መሬት ተጠሪ ከሶስት ዓመት በፊት የአመልካቾቹ አባት ከሞቱ ወዲህ ሽማግሌዎች በተገኙበት ለአመልካቾች ድርሻቸውን ለይተው መስጠታቸውንና አመልካቾችም በተሰጣቸው መሬት ላይ ቤት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የገነቡበት መሆኑን በተደረገው ማጣራት ሊረጋገጠት መቻሉን እንዲሁም ሌላኛው መሬት 2ኛ አመልካች አባቱ በህይወት እያለ ጀምሮ ይዞ እየተጠቀመበት የቆየ መሬት እንጂ አመልካቾች በጉልበት እንዳልያዙ በማረጋገጥ በውጤት ደረጃ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ በማጽናት ወሰኗል፡፡ ከዚህም መረዳት እንደሚቻለው በስር ወረዳም ሆነ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባደረጉት ማጣራት አመልካቾች ወላጆቻቸው በህይወት እየሉ ጭምር ለክርክር ምክንያት የሆኑት መሬቶች ይዘው ሲጠቀሙ የቆዩት መሬት እንደሆነ ተጠሪ ይህንኑ አመልካቾች ይዘውት የሚገኘው መሬት ከአባታቸው ሞት በኋላም ሽማግሌዎች በተገኙበት ለአመልካቾች ድርሻቸውን ለይተው የሰጡዋቸው መሆኑን እንጂ አመልካቾች በጉልበት አለመያዛቸውን የተረጋገጠ ፍሬ ነገር መሆኑን ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካቾች ተጠሪ ሽማግሌ በተገኙበት ድርሻችን በመስጠት ተካፍለናል በሚል የስር መልሳቸው ባልተከራከሩበት ሁኔታ ከጭብጥ ውጪ በመውጣት የተሰጠ ውሳኔ ነው በሚል የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔን የመሻሩን አግባብነት ሲታይ አመልካቾች ተጠሪ ድርሻችን በስምምነት ሰጥታናለች በሚል ባይከራከሩም አከራካሪው የመሬት ይዞታ በጉልበት የያዝነው ሳይሆን ወላጆቻችን በህይወት እያሉ ስንጠቀምበት የቆየን መሬት ነው በሚል የተከራከሩ በመሆኑ የስር ወረዳው ፍርድ ቤትም ባደረገው ማጣራት አመልካቾች በጉልበት አለመያዛቸውን እስከተረጋገጠ ድረስና ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱም ይህንኑ በማጠናከር መልኩ አመልካቾች ከአባታቸው ሞት በኋላም ተጠሪ አመልካቾች የያዙት ይዞታ ድርሻቸው እንዲሆን በሽማግሌዎች ፊት መስማማታቸውንና በጉልበት እንዳልያዙ ላረጋግጥ ችያለሁ ማለቱ ከጭብጥ ውጪ ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ በመሆኑም በወረዳውና በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በማድረግና ወደ ቦታው ድረስ በመሄድ ባደረጉት ተጨማሪ ማጣራት ክርክር ያስነሳሱት መሬቶች አመልካቾች ሟች አባታቸው በህይወት እያሉም ጭምር ተሰጥቷቸው ይዘው ሲጠቀሙበት የነበረ እንጂ በጉልበት መሬቱን አለመያዛቸውን እስከተረጋገጠ ድረስ ሊለቁ አይገባም ተብሎ መወሰኑ ተገቢ ሆኖ እያለ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይህንን በማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር ወደ ጎን በመተው አመልካቾች አከራካሪው ይዞታ ለቀው ለተጠሪ ሊያስረክቡ ይገባል፡፡ ወደሚል ድምዳሜ መድረሱ የማስረጃ ምዘና መርህ ባለመከተል መወሰኑ የሚያሳይ ሲሆን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም ይህንኑ ማረም ሲገባው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ ማጽናቱ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች በአዋጅ ቁጥር 1234 /2013 አንቀጽ 2/4/ሸ/ እና 10 /1/ሐ/ስር በተደነገገው መሰረት ሊታረም የሚገባው መሰረታዊ የህግ ስህተት መፈጸማቸውን የሚያሳይ በመሆኑ ስለሆነ ተከታዮን ወስነናል፡፡

**ውሳኔ ፡፡**

1. የሲዳማ ብ/ክ/መ/ጠ/ቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 04132 በቀን 18/04/2015 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም ይህንኑ ውሳኔ ለማጽናት የክልል ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 04896 በቀን 30/07/2015 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስነስርአት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1/ መሰረት ተሸሯል ።

2. የቡርሳ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 13444 በቀን 18/08/2014 ዓ/ም የሰጡት ውሳኔ እና የበንሳ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 05295 በቀን 06/12/2014 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ ጸንቷል።

3. የዚህ ችሎት ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ።

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ/ጋ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የሠ/መ/ቁጥር 248037

ጥቅምት 05 ቀን 2017 ዓ/ም

ዳኞች ፡- ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ብርሃኑ መንግሥቱ

ማርታ ተካ

አመልካች ፡- ወ/ሮ ብርቂ እዉነቱ

ተጠሪ ፡- ወ/ሮ እቴነሽ ዋለ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የመሬት ይዞታ መብት በሚመለከት የተሰጠ ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል የቀረበ የሰበር አቤቱታ ተከትሎ የተደረገ ክርክር የሚመለከት ነዉ፡፡ተጠሪ በአማራ ክልል ፎገራ ወረዳ ፍርድ ቤት በአመልካች(በስር 2ኛ ተከሳሽ) ላይ እና በስር 1ኛ ተከሳሽ ወ/ሮ ማሬ ካሳ ላይ የመሰረቱት ክስ በአጭሩ - በፎገራ ወረዳ ወረታ ዙሪያ ቀበሌ በ1989 እና 1996 ዓ/ም በይዞታ መለያ ቁጥር AC 49/23/653 በስማቸዉ ተመዝግቦ በክሱ በተገለጸዉ አዋሳኙ ዉስጥ ከሚገኘዉ ሁለት ቃዳ መሬታቸዉ ላይ አዋሳኙ የተገለጸዉን አንድ ቃዳ መሬታቸዉን በቀን 18/10/1997 ዓ/ም በተጻፈ የመሬት ኪራይ ዉል የስር 1ኛ ተከሳሽ ለ13 ዓመት ብር 15,000.00 ከፍለዉ እንዲጠቀሙ ሰጥቻቸዉ ጊዜዉ ከተጠናቀቀ በኋላ ለመልቀቅ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ፈቃደኛ አልሆኑም። ይልቁንም ለአሁን አመልካች አስተላልፈዉ አመልካች የተለያዩ ግንባታዎችን ገንብተዉ ይዘዋል። ስለሆነም ግንባታዉን አፍርሰዉ መሬቱን እንዲለቁልኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል።

የስር 1ኛ ተከሳሽ ቀርበዉ እንዳልተከራከሩ የወረዳዉ ፍርድ ቤት ዉሳኔ ያሳያል።የአሁን አመልካች በሰጡት መልስ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን መሬት የስር 1ኛ ተከሳሽ ቤትና ቦታ ያለበትን በስማቸዉ በሕጋዊ መንገድ ካርታ እና ፕላን የተመዘገበዉን ሕጋዊነቱን በማረጋገጥ በፎገራ ወረዳ ፍትህ ጽ/ቤት በቁጥር ፎ/ወ/ፍት/781 በቀን 03/11/1999ዓ/ም ተረጋግጦ በተመዘገበ ዉል በመግዛት ለወረታ ከተማ ማዘጋጃ ቤት አቅርበዉ በኩል ተቃዋሚ ካለ እንዲቀርብ በማስታወቂያ ጥሪ ተደርጎ ተቃዋሚ ባለመቅረቡ በሕጋዊ መንገድ ወደ በካርታና ፕላን ተመዝግቦ በስማቸዉ ዞሮ የያዙት እንደሆነ በመግለጽ ክሱ ዉድቅ ይደረግልን በማለት ተከራክረዋል።

የወረዳዉ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 35935 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮና ምስክሮቻቸዉ ሰምቶ በሰጠዉ ዉሳኔ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ መሬት በ1989ዓ/ም ለተጠሪ የተደለደለ መሆኑ ተረጋግጧል።በተጠሪ ምስክሮች ቃል እና በማስረጃነት ከቀረበዉ የኪራይ ዉል ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን መሬት የስር 1ኛ ተከሳሽ ሊይዙ የቻሉት በቀን 18/10/1997 ዓ/ም በተደረገ ዉል ለ13 ዓመት እንዲገለገሉ ተጠሪ ብር 15,000.00 ተቀብለዉ በኪራይ ስለአስተላለፉላቸዉ እንደሆነ ተረጋግጧል።በማስረጃነት የቀረበዉ የኪራይ ዉል ርእስ የገጠር መሬት ኪራይ ዉል የሚል ሲሆን ተከራይ 0.235 ሄክታር የገጠር መሬት ለመናፈሻ አገልግሎት በሚል የተከራየች መሆኑንና አከራይም መሬቱን ለገጠር ኢንቨስትመንት ተግባር ያከራየች መሆኑን የዉሉ አንቀጽ 3(1.2) ያሳያል።በዉሉ አንቀጽ 5(2.3.4.5) መሰረት ተከራይ በመሬቱ ላይ ቤትን ከመገንባት ጀምሮ የተለያዩ ሥራዎች መስራት እንደሚችሉ ተመልክቷል።ዉሉ የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 280/1994ን የተከተለ ነዉ።ከገጠር መሬት ይዞታ ጋር በተያያዘም የመሬት ኪራይ ዉሉ በወቅቱ የነበረዉን የክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 46/1992 በኢንቨስትመንት ካልሆነ በስተቀር የገጠር መሬት በኪራይ ዉል በቋሚነት ከአንዱ ባለይዞታ ወደሌላ ባለይዞታ ማዛወር እንደማይቻል ደንግጓል። ይህም ማለት በኪራይ ዉሉ ላይ የተገለጸዉ የኪራይ ዘመን ሲያልቅ መሬቱ በተከራይ ወደ አከራይ ይመለሳል ማለት ነዉ።ነገር ግን መሬቱ ሥልጣን ባለዉ አካል ፍቃድ መሰረት ለኢንቨስትመንት ተብሎ ከባለይዞታዉ ወደሚያለማዉ ኢንቨስተር ከተዛወረ መሬቱ በቋሚነት ወደ ባለሀብቱ ወይም ኢንቨስተሩ ስለሚዘዋወር ወደ መሬቱ ለባለይዞታዉ የሚመለስበት ሁኔታ የለም።በተያዘዉ ጉዳይ ምንም እንኳን በስምምነቱ ዉስጥ የኪራይ ዘመኑ ባይገለጽም የስር 1ኛ ተከሳሽ እና ከተጠሪና ከባለቤታቸዉ ክስ የቀረበበትን መሬት ለኢንቨስትመንት በሚል ብር 15,000.00 በመክፈል በወቅቱ ሥልጣን ባለዉ አካል ፊት የተከራዩ መሆኑ ተረጋግጧል።ይህም የሚያሳየዉ መሬቱ በቋሚነት ከተጠሪ እና ከባለቤታቸዉ ወደ ስር 1ኛ ተከሳሽ መተላለፉን ነዉ።በዚህ መልኩ መሬቱ ወደ ስር 1ኛ ተከሳሽ ከተላለፈ በኋላ በመሬቱ ላይ ተገቢዉን ክፍያ በመፈጸምና ሥልጣን ያለዉን አካል በማስፈቀድ በመሬቱ ላይ የልማት ሥራ በመስራት አስፈላጊ የሆኑ የሰነድ ማስረጃዎችን መያዝ ችለዋል።በመቀጠል በአመልካች ምስክሮች እንደተመሰከረዉና በማስረጃነት ከቀረበዉ የሽያጭ ዉል እንደተረጋገጠዉ የስር 1ኛ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ተከሳሽ አስፈላጊ የሆኑ የሰነድ ማስረጃዎች አቅርበዉ በመሬቱ ላይ ያለዉን ቤትና ቦታ ለአመልካች በሽያጭ አስተላልፈዋል፡፡የወረታ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ሽያጩን ያጸደቀዉ ለመሆኑ ተያይዞ ከቀረበዉ ማስረጃ መረዳት ተችሏል፡፡ አመልካችም በቦታዉ ላይ ካርታ እና ፕላን በስማቸዉ በማሰራት የያዙ ስለመሆኑ ካቀረቡት ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ በዚህ መልኩ ከተጠሪ ወደ 1ኛ ተከሳሽ እንዲሁም ከስር 1ኛ ተከሳሽ ወደ አመልካች የተላለፈበት አግባብ ሕጋዊ መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ መሬት በተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ቢሆንም ከ1989ዓ/ም በተሰሩት ሥራዎች ወደ 1ኛ ተከሳሽ ቀጥሎም ወደ አሁን አመልካች ስለተላለፈ በተጠሪ ስም መመዝገቡ ተቀባይነት የለዉም፡፡ስለሆነም ተጠሪ አመልካች በመሬቱ ላይ የገነቡትን ግንባታ ለቀዉ እንዲያስረክቡ በማለት ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለዉም በማለት ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

ተጠሪ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዉ ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 79869 ላይ አከራክሮና የግራ ቀኙን ማስረጃ በድጋሚ በመመዘን በቀን 16/09/2014ዓ/ም በሰጠዉ ፍርድ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ጉድለት የለበትም በማለት አጽንቷል፡፡ በመቀጠል ተጠሪ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርበዉ ችሎቱም ግራ ቀኙን በመ/ቁጥር 03-115895 ላይ አከራክሮ በቀን 30/06/2015ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ መሬት በ1989 ዓ/ም ለተጠሪ በእርሻ መሬትነት እንደተሰጠ ከተረጋገጠ በምን ሕጋዊ አግባብ አመልካች መያዛቸዉ ተረጋግጦ ነዉ የተጠሪ ክስ ዉድቅ የተደረገዉ የሚለዉን ጭብጥ በመያዝ መርምሮ መሬቱ ለተጠሪ በ1989 ዓም በእርሻ መሬትነት የተሰጠ እና መሬቱ እስካሁን በተጠሪ ስም በሚገኝ ደብተር ላይ የተመለከተ መሆኑን የክፍሉ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት በጻፈዉ ማስረጃ ማረጋገጡን መገንዘብ ተችሏል፡፡ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 133/1998 አንቀጽ 15 እና 18 መሰረት በኪራይ መስጠት የሚችሉ ቢሆንም በሕግ በተደነገገዉ አግባብ ተጠሪ ከእርሻ መሬቱ መነሳታቸዉ  አልተረጋገጠም፡፡ተጠሪ የእርሻ መሬቱ ላይ ያላቸዉን መብት አጥተዋል ተብሎ የተሰጠዉ ዉሳኔ በሕገ መንግሥቱና በመሬት አዋጁ የተደነገገዉን የመሬት በገንዘብ ያለመሸጥ ድንጋጌ የሚቃረን ነዉ፡፡አመልካች ከስር 1ኛ ተከሳሽ ጋር ያደረጉት ዉል በተተሪ የእርሻ መሬት ይዞታና በሕግ ከተደነገገዉ ዉጭ ወደ ሌላ ሦስተኛ ወገን ሊተላለፍ በማይችል የእርሻ መሬት ይዞታ ላይ በመሆኑ ዉሉም አመልካች በቅን ልቦና የፈጸሙት ነዉ የሚለዉ መከራከሪያ ተቀባይነት የለዉም፡፡አመልካች መሬቱን የያዙት መብት ከሌላቸዉ ሰዉ ጋር ዉል ፈጽመዉ ስለሆነና ዉሉም የመሬቱን ሕጋዊ ባለይዞታ የማያስገድድ ስለሆነ አመልካች የፈጸሙትን ግንባታ አፍርሰዉ ክስ የቀረበበትን መሬት ለተጠሪ ሊለቁ ይገባል በማለት የስር ፍርድ ቤቶችን ዉሳኔ ሽሯል፡፡

አመልካች በቀን 28/09/2015 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በክልሉ ሰበር ችሎት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ሲሆን የአቤቱታቸዉ አጭር ይዘት፡-የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት መሬቱ የገጠር እርሻ መሬት ነዉ በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ የስር ከፍተኛ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ፍርድ ቤት የገጠር መሬት ነዉ ወይስ የከተማ መሬት ነዉ የሚለዉ ተጣርቶ እንዲቀርብ በሰጠዉ ትእዛዝ መሰረት ተጣርቶ በቁጥር 566/1/14 በቀን 19/08/2014 ዓ/ም በተጻፈ ማስረጃ መሬቱ ወደ ወረታ ከተማ ማስተር ፕላን ዉስጥ ገብቷል የሚለዉን ወደ ጎን የተወ ነዉ፡፡ይህም የሆነዉ ተጠሪ በዘላቂነት ካሳ ተከፍሏቸዉ መሬቱን ከመልቀቃቸዉ በፊት ጀምሮ መሬቱ የከተማ ቦታ መሆኑን የሚያሳይ ነዉ፡፡በተጠሪ እና በስር 1ኛ ተከሳሽ ጋር የነበረዉ ዉል ርዕሱ የኪራይ ዉል ይበል እንጂ የኪራይ ዉል ይዘት የሌለዉ፤ዉሉ የሚያበቃበት ጊዜ ያልተቀመጠ ይልቁንም በዘላቂነት ካሳ ተከፍሏቸዉ ተጠሪ መሬቱን እንዳስረከቡ በወረዳዉና በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ነዉ፡፡አዋጅ ቁጥር 133/1998 ከመጽናቱ በፊት ለተደረገ ዉል የክልሉ ሰበር የአዋጁነእ አንቀጽ 15 እና 18ን በመጥቀስ ዉሳኔ መስጠቱ ሕጉ ወደኋላ እንዲሰራ ያደረገ በመሆኑ የሕግ ጥሰት ነዉ፡፡ተጠሪ በክሳቸዉ ላይ እንደገለጹት ከነበራቸዉ ሁለት ቃዳ ዉስጥ አንዱን ቃዳ በ1997 ዓ/ም በማስተላለፋቸዉ የቀራቸዉ አንድ ቃዳ በመሆኑ በስማቸዉ የተመዘገበዉ ይሄዉ አንድ ቃዳ ሆኖ እያለ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ በተጠሪ ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ በማድረግ የሰጠዉ ዉሳኔ ስህተት ነዉ፡፡የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች የቅን ልቦና ገዥ እንዳልሆንኩ አድርጎ የወሰነዉ የገጠር መሬት እንደገዛሁ አድርጎ ቢሆንም በወረዳ እና በከፍተኛ ፍርድ ቤት እንደተረጋገጠዉ መሬቱ ወደ አመልካች ሲተላለፍ መሬቱ የእርሻ መሬት ሳይሆን የከተማ ቦታ ነዉ፡፡ ካርታ እና ፕላን አለዉ፡፡ቦታዉ የስር 1ኛ ተከሳሽ መሆኑ ተረጋግጦ በአመልካችና በስር 1ኛ ተከሳሽ መካከል የተደረገዉ ዉል በወረዳዉ ፍትህ ጽ/ቤት በቁጥር ፎ/ወ/ፍት/781 በቀን 03/11/1999ዓ/ም ጸድቋል፡፡ ማዘጋጃ ቤቱም በሻጭ ስም ያለዉን ቤትና ቦታ አመልካች በገዛሁት መሰረት በካርታ አረጋግጦ ስመ ንብረቱን ከሻጭ ወደ ገዥ አዛዉሮልኝ እያለ የክልሉ ሰበር የእርሻ መሬት እንደገዛሁ አድርጎ የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ ይሻርልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

ችሎቱ አቤቱታዉንና በየደረጃዉ የክልሉ ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ዉሳኔዎች በመመርመር ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ መሬት በወረታ ከተማ ክልል የሚገኝ ስለመሆኑና የቀድሞ ሻጭ ለመናፈሻ አገልግሎት ግንባታ አከናዉነዉና የይዞታ ማረጋገጫ አግኝተዉ ለአመልካች ማስተላለፋቸዉ እንዲሁም አመልካች በቦታዉ ላይ ግንባታ ያከናወኑት መሬቱ በከተማ አስተዳደር የይዞታ ማረጋገጫ በስማቸዉ ተሰጥቷቸዉ መሆኑን የስር ፍርድ ቤቶች አረጋግጠዉ የሰጡትን ዉሳኔ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የገጠር መሬት ሽያጭ ስለሆነ አመልካች ግንባታዉን አፍርሰዉ መሬቱን ይልቀቁ በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ በሰ/መ/ቁጥር 55273 ፤63014 እና በሌሎች መዛግብት ላይ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ከሰጠዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም አንጻር እንዲመረመር ተጠሪ መልስ እንዲሰጡ አዝዟል፡፡

ተጠሪ በቀን 12/07/2016ዓ/ም በተጻፈ መልሳቸዉ - አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 27/3 ስር የተደነገገዉ የአቤቱታ ማቅረቢያ 90 ቀን ካለፈ በኋላ ስለሆነ አቤቱታቸዉ ዉድቅ ሊሆን ይገባል፡፡ አመልካች መሬቱ ገዛሁኝ በሚሉበት ጊዜ መሬቱ በተጠሪ ይዞታ ስር ሆኖ በገጠር

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የእርሻ መሬትነት ነዉ፡፡በከፍተኛ ፍርድ ቤት በተሰጠ ትእዛዝ የቀረበ ማስረጃ መሬቱ በወረታ ከተማ ማስተር ፕላን ዉስጥ የሚተዳደር ነዉ ብሎ ከመግለጹ በስተቀር አመልካች መሬቱን አገኘሁበት ባሉበት ወቅትም ሆነ ክስ በቀረበበት ጊዜ መሬቱ በማን ይተዳደር እንደነበር አላረጋገጠም፡፡ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ መሬት በ1989 ዓ/ም ለተጠሪ የተሰጠ መሆኑ እና በይዞታ መለያ ቁጥር AC 49/23/653 በሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር ይዘዉ የሚጠቀሙበት መሆኑን የወረዳዉ ፍርድ ቤት በትእዛዝ ባስቀረበዉ ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡መሬቱ ወደ ወረታ ከተማ ክልል የገባዉ ከመቼ ጀምሮ እንደሆነ የከተማዉ አስተዳደር እንዲገልጽ ታዝዞ መሬቱን የሚያስተዳድረዉ የፎገራ ወረዳ ፍርድ ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ስለሆነ አይመለከተኝም የሚል ምላሽ ሰጥቷል፡፡በዚህ መልኩ መሬቱ የእርሻ መሬት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡የወረታ ከተማ አስተዳደር ካሳ ከፍሎ መሬቱን ያስለቀቀ ስለመሆኑ ምንም የቀረበ ማስረጃ የለም፡፡መሬቱ በከተማ አስተዳደር ስር የነበረ ቢሆን ኖሮ ተጠሪ የኪራይ ዉል መዋዋል አልችልም ነበር፡፡በቀን 18/10/1997ዓ/ም የተደረገዉ የኪራይ ዉል ተከራይ መሬቱን በእንክብካቤ ተጠቅመዉ የ13 ዓመት የዉል ዘመኑ ሳይጠናቀቅ ለተጠሪ እንደሚመልሱ የሚገልጽ ነዉ፡፡ አመልካች መሬቱን በግዥ አገኘሁኝ የሚል ክርክር በማቅረባቸዉ የክልሉ ሰበር ችሎት አዋጅ ቁጥር 133/1998 መሰረት በማድረግ ዉሳኔ መስጠቱ ተገቢ ነዉ፡፡ተጠሪ ያለኝ ሁለት ቃዳ መሬት ሲሆን ክስ የመሰረትኩት በአመልካች በተያዘዉ አንድ ቃዳ መሬት ላይ ነዉ፡፡በተጠሪ ስም የተመዘገበዉ የይዞታ ማረጋገጫ የሚያሳየዉ ሁለት ቃዳ መሬት መሆኑን ስለሚያሳይ የይዞታ ማረጋገጫዉ እስካልተሰረዘ ድረስ ዋጋ ያለዉ ነዉ፡፡የኪራይ ዉሉ በወረዳዉ ግብርና እና ገጠር ልማት ጽ/ቤት የተመዘገበ ሲሆን በዉሉ ላይ እማኝ የነበሩ ምስክሮች ዉሉ ለ13 ዓመት የተደረገ መሆኑን አስረድተዋል፡፡የስር 1ኛ ተከሳሽ ይህንን መሬት ከተከራዩ በኋላ በስማቸዉ የተሰራ የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ የለም፡፡ይህ መሬት ከተጠሪ ወደ ስር 1ኛ ተከሳሽ ስመ ንብረት ዝዉዉር አልተፈጸመም፡፡ይህንን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አልቀረበም፡፡የስር 1ኛ ተከሳሽ ቦታዉን ወደ አመልካች ለማስተላለፍ መጀመሪያ የማስተላለፍ መብት ሊኖራቸዉ ይገባል፡፡ስለሆነም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤቶችን ዉሳኔ በመሻር አመልካች መሬቱን እንዲለቁ በመወሰኑ የተፈጸመ ስህተት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካችም የመልስ መልሳቸዉን በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ከላይ አጠር ባለመልኩ የተገለጸዉ የግራ ቀኙን ክርክርና በየደረጃዉ ባሉት የክልሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት የሚመለከት ሲሆን እኛም ከፍ ሲል የተያዘዉን ጭብጥ መሠረት በማድረግ አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

በመጀመሪያም ተጠሪ አመልካች የሰበር አቤቱታቸዉን በሕጉ መሠረት በ90 ቀናት ዉስጥ ያላቀረቡ በመሆኑ ተቀባይነት ሊኖረዉ አይገባም በማለት ያቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መርምረናል፡፡ ተጠሪ የሰበር አቤቱታዉ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 27/3 ስር በተደነገገዉ መሠረት የመጨረሻዉ ዉሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት 90 ቀናት ዉስጥ ያልቀረበ ከሆነ ወይም ይህ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ጊዜ ካለፈ በኋላ የቀረበ የሰበር አቤቱታ ከሆነ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት አንስተዉ መከራከር እንደሚችሉ በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 8(5/ሀ) ስር ተመልክቷል፡፡በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡበት የመጨረሻ ዉሳኔ በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተወሰነዉ በቀን 30/06/2015ዓ/ም ሲሆን አመልካች ለዚህ ሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ደግሞ በቀን 28/9/2015 ዓ/ም እንደሆነ አረጋግጠናል፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለዉ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት የመጨረሻዉ ዉሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት 90 ቀናት ዉስጥ መሆኑን ነዉ፡፡ስለሆነም ተጠሪ ከዚህ አኳያ ያቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አልተቀበልንም፡፡

ዋናዉን ጉዳይ እንደመረመርነዉ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ መሬት በ1989 ዓ/ም በድልድል ለተጠሪ የተሰጣቸዉ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡በዚህ መልኩ ለተጠሪ በድልድል የተሰጠዉና በስማቸዉ ተመዝግቦ የሚገኘዉ ሁለት ቃዳ መሬት ሲሆን ከዚህ መሬት ላይ አከራካሪ የሆነዉ መሬት አንድ ቃዳ መሬት መሆኑም በግራ ቀኙ የታመነ ነዉ፡፡ይህን መሬት ተጠሪ በቀን 18/10/1997 ዓ/ም በተደረገ ዉል ለስር 1ኛ ተከሳሽ ወ/ሮ ማሬ ካሴ ማስተላለፋቸዉ ዉሉም በወቅቱ በሕግ ሥልጣን በተሰጠዉ በፎገራ ወረዳ ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት የተመዘገበ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ከዚህ መገንዘብ የሚቻለዉ ይህ ዉል በተፈጸመበት ጊዜ መሬቱ የገጠር መሬት እንደነበረ ነዉ፡፡ ከዚህ ዉል ጋር በተያያዘ ግራ ቀኙን ያከራከረዉ ጉዳይ ተጠሪ መሬቱን ለስር 1ኛ ተከሳሽ ያስተላለፉት በአጭር ጊዜ በሚቆይ ኪራይ ነዉ ወይስ በቋሚነት ነዉ?በቋሚነት ነዉ የሚባል ከሆነ በዚህ አግባብ የሚደረግ ዉል የሚኖረዉ ሕጋዊ ዉጤት ምንድን ነዉ የሚል ነዉ፡፡

በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40/3 ስር እንደተደነገገዉ እና በተጠሪ እና በስር 1ኛ ተከሳሽ መካከል በቀን 18/10/1997ዓ/ም ዉል በተደረገ ጊዜ ተፈጻሚ ሲሆን በነበረዉ የአማራ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 46/1992 አንቀጽ 6/1 ስር እንደተደነገገዉ መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ መንግስትና ሕዝቦች የጋራ ሀብት ነዉ፡፡በተጠሪ እና በስር 1ኛ ተከሳሽ መካከል የተደረገዉ ዉል ርዕሱ የኪራይ ዉል የሚል ቢሆንም በሕግ ማስረጃ የመመርመርና የመመዘን ሥልጣን በተሰጣቸዉ የወረዳ ፍርድ ቤት እና የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዉሉ ይዘት ተመርምሮ ድምዳሜ ላይ እንደተደረሰዉ አከራካሪዉን መሬት ከስር 1ኛ ተከሳሽ በቋሚነት(ላልተወሰነ ጊዜ) ለመናፈሻ አገልግሎት ኢንቨስትመንት ለማዋል ለተጠሪ ብር 15,000.00 ከፍለዉ ያገኙት መሬት እንደሆነ ተረጋግጧል፡፡በዚህ መልኩ ክፍያ በመቀበል የገጠር መሬት ባለይዞታ የእርሻ መሬቱን ለሌላ ግለሰብ በቋሚነት ለማስተላለፍ የሚያደርገዉ ዉል ብቻዉን ሲታይ በኪራይ ዉል ሰበብ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40/4 ስር ጥበቃ የተደረገለትን የአርሶ አደሮችን ከመሬታቸዉ ያለመፈናቀል መብት የሚጥስ በመሆኑ ተቀባይነት ሊኖረዉ የሚገባ አይደለም፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በሌላ በኩል በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40/8 ላይ እንደተመለከተዉ በመሬቱ ላይ ለተፈራዉ ሀብት መንግሥት ተመጣጣኝ ካሳ በመክፈል የከተማም ሆነ የገጠር መሬት ለተሻለ የሕዝብ ጥቅም እንዲዉል ማድረግ ይችላል፡፡በተያዘዉ ጉዳይ በተጠሪና በስር 1ኛ ተከሳሽ መካከል የተደረገዉ ዉል በቀን 09/03/1998ዓ/ም በፎገራ ወረዳ ግብራናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት መጽደቁ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ጽ/ቤቱ ዉሉን ያጸደቀዉ በኢንቨስትመንት ዉል ማጽደቂያ ቅጽ እንደሆነ፤መሬቱ በዘላቂነት ለመናፈሻ አገልግሎት እንዲዉል በመፈለጉና ተጠሪ መሬቱን ለለቀቁበት ብር 15,000.00 ማካካሻ እንደተከፈላቸዉ፤ የስር 1ኛ ተከሳሽ መሬቱን ለታለመለት ኢንቨስትመንት ዓላማ ሊያዉሉ እንደሚገባ እና በተጠሪ ስም በተመዘገበዉ የመሬት መጠቀሚያ ጊዜያዊ ሰርተፊኬት ላይም ይህ በኪራይ የተላለፈዉ መሬት እንደተነሳ በመግለጽ እንዳጸደቀዉ በማጽደቅያዉ መሸኛ ላይ በመግለጽ እንደሆነ የስር ወረዳ ፍርድ ቤት ካረጋገጠዉ መገንዘብ ተችሏል፡፡ይህም የሚያሳየን አከራካሪዉ መሬት በወቅቱ መሬቱን በሚያስተዳድረዉ የአስተዳደር አካል እዉቅናና አጽዳቅነት ተጠሪ የተስማሙበት "ካሳ" ተከፍሏቸዉ የስር 1ኛ ተከሳሽ መሬቱን በኢንቨስትመንት ለመናፈሻ አገልግሎት እንዲያዉሉት እንደተሰጣቸዉ ነዉ፡፡

ዉሉ በተደረገበት ወቅት በአማራ ክልል ተፈጻሚ ሲሆን በነበረዉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ለመወሰን በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 46/1992 አንቀጽ 6/4 ስር እንደተመለከተዉ ማንኛዉም አርሶ አደር… ወይም የገጠር መሬት ባለይዞታ የሆነ ሰዉ ከግለሰብ ወይም ከባለሀብት…ጋር ዉል በመዋዋል መሬቱን የማከራት መብት አለዉ፡፡እንዲሁም ከኢንቨስትመንት ጋር በተያያዘም በአርሶ አደሩና በኢንቨስተሩ መካከል በሚደረጉ ስምምነቶች መሠረት የሚዉሉ መሬቶችን በተመለከተ በዚህ አዋጅ በተደነገገዉና በሁለቱ ወገኖች መካከል በሚደረግ ሕጋዊ ዉል መሠረት ሊፈጸም እንደሚችል በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 15/2 ስር ተደንግጓል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች እና በወቅቱ ተግባራዊ ሲሆን በነበረዉ ለመንግሥት ሥራዎች መሬት የሚለቀቅበትንና ለንብረት ካሳ የሚከፈልበትን ሁኔታዎች ለመወሰን በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 401/1996 ላይ ከተደነገገዉ መረዳት የሚቻለዉ በመርህ ደረጃ አንድ መሬት ለሕዝብ ጥቅም እንዲዉል ተፈልጎ ባለይዞታዉ እንዲለቅ ሲደረግ መሬቱን ማስለቀቅ ያለበትና ካሳ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ያስለቀቀዉ የመንግሥት አካል ቢሆንም አከራካሪዉ መሬት በመንግሥት አነሳሽነት ተጠሪ እንዲለቁ የተደረገ ባለመሆኑ ወይም ደግሞ መሬቱ በተገለጸዉ መልኩ ለኢንቨስትመንት እንዲዉል የተደረገዉ ለግል ኢንቨስትመነት እንደመሆኑ ለተጠሪ የተከፈለዉ ብር 15,000.00 በመንግሥት አስተዳደር አካል እዉቅና ጭምር የተከፈለ በመሆኑ ካሳ ነዉ ሊባል ከሚችል በስተቀር የመሬት ሽያጭ ክፍያ ነዉ ብሎ ለመደምደም የሚያስችል አሳማኝ ምክንያት የለም፡፡

ዉሉ በጸደቀበት ጊዜ በነበረዉ አዋጅ ቁጥር 455/1997 አንጻር ሲታይም በቀጥታ መንግስት ለሕዝብ ጥቅም ተጠሪ መሬቱን እንዲለቁ ተደርጓል የሚል ድምዳሜ ላይ መድረስ ባይቻልም በመሬቱ ላይ የስር 1ኛ ተከሳሽ ኢንቨስት እንዲያደርጉ በወቅቱ ሥልጣን በተሰጠዉ አስተዳደር አካል አጽዳቅነት እንደተላለፈላቸዉ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

እስከተረጋገጠ ድረስ ገንዘቡን መንግሥት ባለመክፈሉ ብቻ ለተጠሪ የተከፈለዉ ገንዘብ የካሳ ገንዘብ አይደለም ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ በመሆኑም የስር ወረዳ እና የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች የዉሉን ይዘት እና በወቅቱ ሥልጣን ያለዉ አስተዳደር አካል ዉሉን ተቀብሎ ያጸደቀበትን ዓላማ ከግምት በማስገባት አከራካሪዉ የመሬት ይዞታ ከተጠሪ ወደ ስር 1ኛ ተከሳሽ የተላለፈዉ ተጠሪ በክሳቸዉ ላይ እንደገለጹት ለተወሰነ ጊዜ በተደረገ የኪራይ ዉል ሳይሆን በቋሚነት ለመናፈሻ አገልግሎት ኢንቨስትመንት እንዲዉል ነዉ በማለት የደረሱበት የፍሬ ነገር ድምዳሜ የሕግ  ድጋፍ ያለዉ ነዉ፡፡ በአንጻሩ የክልሉ ሰበር ችሎት ይህ ድምዳሜ የገጠር መሬት በሽያጭ ለማስተላለፍ የተደረገ ዉል ሕጋዊ ዉጤት እንዲኖረዉ የሚያደርግ ድምዳሜ ነዉ ሲል የሰጠዉ ዉሳኔ የተደረገዉን ዉል ይዘት እና የዉሉን አጸዳደቅ ያላገናዘበ ነዉ፡፡

በተጨማሪም ከላይ በተገለጸዉ መሰረት ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን መሬት የስር 1ኛ ተከሳሽ ሲረከቡ መሬቱ የገጠር እርሻ መሬት የነበረ እና በተጠሪ ስም የተመዘገበ መሆኑ ባያከራክርም በዚህ መሬት ላይ የስር 1ኛ ተከሳሽ የተለያዩ ግንባታዎችን በመፈጸም በስማቸዉ ካስመዘገቡ በኂላ መሬት ወደ በስር 1ኛ ተከሳሽ እና በአመልካች መካከል በተደረገ የሽያጭ ዉል ከመፈጸሙ በፊት በስር 1ኛ ተከሳሽ ስም ዞሮ እንደተመዘገበ ፤በመቀጠልም 1ኛ ተከሳሽ በመሬቱ ላይ ከፈጸሙት ግንባታ ጋር ለአሁን አመልካች በሽያጭ ሲያስተላልፉ መሬቱ በከተማ ክልል ገብቶ በአሁን አመልካች ስም በተመዘገበ የምሪት ይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ከ2001 ዓ/ም ጀምሮ ተመዝግቦ እንደሚገኝ የአመልካች ክርክር የሚያሳይ ሲሆን በተጠሪ በኩል ይዞታዉ በዚህ መልኩ በአመልካች ስም አልተመዘገበም የሚል ክርክር አልቀረበም፡፡የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት መሬቱ በዚህ መልኩ ወደ ከተማ ክልል ገብቶ በመጀመሪያ ወደ ስር 1ኛ ተከሳሽ ተላልፎ ቀጥሎም አመልካች ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ ተረጋግጦ የቀረበዉን ፍሬ ነገር ወደ ጎን በመተዉ በተጠሪና በስር 1ኛ ተከሳሽ ዉሉ በተደረገበት ጊዜ መሬቱ የገጠር እርሻ መሬት መሆኑንና በዚያን ጊዜ መሬቱ በተጠሪ ስም ተመዝግቦ የነበረ መሆኑን ብቻ ከግምት በማስገባት አመልካች መሬቱን ያገኙት መብት ከሌላቸዉ 1ኛ ተከሳሽ ላይ ስለሆነ ሊለቁ ይገባል ሲል የደረሰበት ድምዳሜ በአሁኑ ጊዜም ሆነ መሬቱ ወደ አመልካች ሲተላለፍ የመሬቱ አጠቃቀም መለወጡን ያላገናዘበ ዉሳኔ ነዉ፡፡

ሲጠቃለል አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን መሬት ላይ ከተፈጸመዉ ግንባታ ጋር ተገቢዉን ጥንቃቄ አድርገዉ መሬቱን ለማስተላለፍ መብት ከነበራቸዉ ከስር 1ኛ ተከሳሽ ላይ በሕጋዊ መንገድ በሽያጭ አግኝተዉ በስማቸዉ ተመዝግቦ የሚገኝ የከተማ መሬት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ይህ ፍሬ ነገር ተረጋግጦ እያለ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች መሬቱን መብት ከሌላቸዉ ሰዉ ላይ እንዳገኙ እና መሬቱም የገጠር እርሻ መሬት እንደሆነ በመግለጽ አመልካች መሬቱን ሊለቁ ይገባል ሲል የሰጠዉ ዉሳኔ በማስረጃ የተረጋገጠዉን ፍሬ ነገር ያላገነዛበ በመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 80(3/ለ) ስር ከተሰጠዉ ሥልጣን አንጻር ሲታይ የማስረጃ ምዘና መርህ አተገባበር ስህተት የተፈጸመበት ከመሆኑም በተጨማሪ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40 ስር ጥበቃ የተደረገለትን የአመልካችን የንብረት መብት የሚጥስ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በመሆኑ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሀ) እና 10(1/ሐ) መሠረት ሊታረም የሚገባዉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ ብለናል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ዉሳኔ</u>**

1. የፎገራ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 35935 ላይ በቀን 26/11/2013ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 79869 ላይ በቀን 16/09/2014ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 መሰረት ጸንተዋል፡፡
2. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 03-115895 ላይ በቀን 30/06/2015ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 መሰረት ተሽሯል፡፡
3. በዚህ ችሎት የወጣ ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

<u>ማስታወሻ</u>፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መ/ቁ 248089

ጥቅምት 5 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች፡ ብርሃኑ አመነው

በእውቀቱ በላይ

ቀንዓ ቂጣታ

ብርሃኑ መንግስቱ

ማርታ ተካ

አመልካች፡- በአዲስ አበባ ከተማ አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 ኮንስትራክሽን ቤቶች ልማት ፅ/ቤት - አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡- 1ኛ የአቶ ሰለሞን ሀይሉ ወራሾች

ተማሪ ናትናኤል ሰለሞን
ህፃን ማህሌት ሰለሞን / ጠበቃ ሊያ ኪሮስ - ቀረቡ

2ኛ ወ/ሮ ሰዓዳ በላይ - አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

መዝገቡ ለሰበር ችሎት የቀረበዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/303595 ላይ በቀን 19/08/2015ዓ.ም የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ በማጽናት የሰጠዉ ብይን መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ዉሳኔዉ በሰበር ችሎት እንዲታረም አመልካች በቀን 25/09/2015ዓ.ም ባቀረበዉ አቤቱታ መነሻ ነዉ፡፡

ጉዳዩ የመፋለም ክስን የሚመለከት ሲሆን የ1ኛ ተጠሪ ወራሾች በህዳር 24 ቀን 2008ዓ.ም ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ሟች አባታችን በአዲስ አበባ ከተማ አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ6 የቤት ቁጥር 242 የሆነ መኖሪያ ቤት ከወንድማቸው ከአቶ ደበላ በስጦታ በተሰጣቸው ቦታ ላይ በ1965 ዓም ቤት ሰርተው ቁጥር 19/26689 የሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር አውጥተው በመኖር ላይ እያሉ ለስራ አመቺ በሆነ አካባቢ ለመኖር ሲሉ የቤት ቁጥር 242ን ለቀድሞ ወረዳ 19 ቀበሌ 56 አስረክበው በምትክ በአዲስ አበባ ከተማ ወረዳ14 ቀበሌ 25 የቤት ቁጥር 196 የሆነ መኖሪያ ቤት ተረክበው ያለኪራይ ይኖሩ የነበረ ሲሆን ካረፉ በኃላ ወራሽነታችንን አረጋግጠናል፤ሟች አባታችን በምትክ ተስጥቷቸው ኪራይ ሳይከፍሉ ይኖሩበት የነበረው ቤት በሸራተን ሆቴል ማስፋፊያ ፕሮጀክት ስለፈረሰ ወደ ግል ቤት መመለስ የግድ ስለሆነብን የወረዳ6 ኮንስትራክሽን ቤቶች ልማት ፅ/ቤት የቤት ቁጥር 242 ተከራይ የሆኑትን ወ/ሮ ሰዓዳ በላይን በማስለቀቅ ቤቱን እንዲሰጠን በተደጋገሚ ጥያቄ ብናቀርብም ወረዳውም ሆነ ወ/ሮ ሰዓዳ ቤቱን ለቀው ለማስረከብ ፈቃደኛ አይደሉም፡፡ በመሆኑም የአቃ/ቃ/ክ/ከ/ወ/6 ኮንስትራክሽን ቤቶች ልማት ፅ/ቤት ከሟች የተረከበውን የቤት ቁጥር 242 ለ1ኛተጠሪ ወራሾች ይመልስ ተብሎ እንዲወሰን በማለት ያቀረቡ ሲሆን አመልካች ጥር 12 ቀን 2009 ዓ.ም በሰጠዉ መልስ የ1ኛ ተጠሪ ወራሾች የጠየቁት ቤትና ይዞታ ወላጅ አባታቸው በህይወት እያለ ያልያዙትና ያልጠየቁት ነው፤ከሞቱም በኃላ የመጠየቅ መብታቸው በይርጋ ቀሪ ሆኗል፤ወራሽ አውራሹ በያዙትና ባላቸው መብት ከሚጠይቁ በቀር ሟች ትተውት ባለፉት ሊጠይቁ አይችሉም፤የጠየቁትን ቤትና ቦታ የሚያሳይ የባለቤትነት ካርታ አላቀረቡም ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል ሲል ክርክሩን አቅርበዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራቀኙ ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ በመንግስት ቤቶች አስተደደር መመሪያ ቁጥር 4/2009/አንቀፅ 33 ላይ እንደተመለከተው በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ቤቱን ለመንግስት አስረክቦ በማካካሻነት ቤት ተሰጥቶ እየኖረበት ያለውን መንግስት የሚያፈርሰው ከሆነ የእራሱ ቤት ተመልሶለት እንዲኖርበት እንደሚደረግ የተመለከተ መሆኑ 1ኛ ተጠሪ የቤት ቁጥር 242 የሆነውን መኖሪያ ቤት ከወንድማቸው በስጦታ ያገኙት መሆኑን፤የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ያወጡ ስለመሆኑ እና ለከፍተኛ 19 ቀበሌ 55 ያስረክቡ መሆኑን በማካካሻ ያገኙት ቤት በልማት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የፈረሰ ለመሆኑ በቀረቡት የሰነድ ማስረጃዎች ስለተረጋገጠ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/1195(1)፤1206 እንዲሁም በመንግስት ቤቶች አስተዳደር መመሪያ አንቀጽ 33(1) መሰረት አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ ወራሾች ቤቱን እንዲመልስና 2ኛ ተጠሪም እንድታስረክባቸው በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በውሳኔው ላይ ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ፍርድ ቤቱም በስር ፍርድ ቤት ያላነሱትን የመከራከሪያ ነጥብ ለሚመለከተው ቅሬታ ሰሚ ጉባኤ አላቀረቡም በሚል እና ቤቱ መወረሱን አልተከራከሩም ሲል በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/337 መሰረት ይግባኙን ሰርዟል፡፡ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ነዉ፡፡

ስለአመልካች የክፍሉ አቃቤ ህግ በቀን 25/9/2015ዓ.ም ጽፎ ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ይዘትም ባጭሩ:የ1ኛ ተጠሪ ወራሾች መጠየቅ ያለባቸው አመልካችን ሳይሆን የቂርቆስ ክፍለ ከተማ አስተዳደርን ነው፤በሟች አባታቸውና በአስተዳደሩ መካከል የተደረገውን የቤት ለውጥ ስምምነት አላሻሩም ይህ ስምምነት እስካልተሻረ ድረስ የቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም፤የ1ኛ ተጠሪ ወራሾች ያቀረቡት የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ ለአባታቸው ቅያሪ ከመሰጠቱ በፊት የተሰጠ ካርታ ሲሆን በፍ/ብ/ህ/ቁ/1195 መሰረት ለአመልካች የተሰጠው የባለቤትነት ማረጋገጫ አልተሻረም፤ይህ ባልሆነበት የመፋለም ክስ ማቅረባቸው አግባብነት የለውም፤የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰ/መ/ቁ/23331 (ቅፅ7) በሰጠው አስገዳጅ ትርጉም መሰረት ስምምነት ባልተሸረበት የሚቀረበው አቤቱታ አግባብነት የለውም፤2ኛተጠሪ ቤቱን ከመንግስት ተከራይታ ያለች ሲሆን በቤቶች መመሪያ ቁጥር 6/2015 እና የፌዴሬሽን ምክር ቤት በመስከረም 29/2011 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ መሰረት በመንግስት ቤትነት ከመቀጠል ውጭ የግለሰብ ቤት የሚሆንበት ምንም የህግ አግባብ የለም፤በመሆኑም የ1ኛተጠሪ ወራሾች የቤታቸውን ምትክና ካሳ ቤታቸውን ያፈረሰው አስተዳደር አካል ከመጠየቅ ውጭ አመልካችን ሊጠይቁ አይገባም ተብሎ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡

የሰበር ችሎቱ የአመልካች አቤቱታ ተመልክቶ በመጋቢት 24 ቀን 2016 በሰጠው ትዕዛዝ ቤቱ የፈረሰዉ በቂርቆስ ክ/ከተማ ነዉ በሚል ቂ/ክ/ከተማ ወደ ክርክሩ እንዲገባ የተጠየቀዉ ዳኝነት እንዲሁም በሁለቱ መካከል የተደረገው የቤት ለውጥ ውል ባልፈረሰበት አመልካች ሊከሰስ አይገባም በሚል የቀረበው ክርከር የታለፈበትን አግባብ ከክርክር አመራር ስነ-ስርዓት እንዲሁም በመ/ቁ/23331 (ቅፅ7) ላይ ከተሰጠው ገዥ ውሳኔ አኳያ ለመርመር ተጠሪዎች መልሳቸውን እንዲያቀርቡ ትዕዛዝ ሰጥቶ የ1ኛተጠሪ ወራሾች በሚያዝያ 21 ቀን 2016 ዓ.ም መልስ ያቀረቡ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ሲሆን ይዞቱም የቂርቆስ ክፍለ ከተማ አስተዳደር መሬት ልማት ባንክና ከተማ ማደስ ፕሮጀክት ፅ/ቤት አመልካች ቤቱን ለ1ኛ ተጠሪ ወራሾች እንዲያስረክብ በቀን 27/7/2003ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር ቂ/ክ/ከ/መ/ል/ባ/ከ/ማ/ፕ/953/03 በፈቀደበት ሁኔታ አመልካች የቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወደ ክርክሩ ሊገባ ይገባል ሲል ያቀረበው ክርክር አግባብነት የለውም፤አመልካች በቤቱ ላይ የቤት ለውጥ ውል ስለመደረጉ በምንም አይነት ማስረጃ አላስረዱም፤ውሉ አልፈረሰም የሚለው ክርክር የህግም ሆነ የማስረጃ መሰረት የለውም፤ በቅፅ 7 በሰ/መ/ቁ/23331 የተሰጠው ውሳኔ በሽያጭ የተገዛ ቤትን የሚመለከት ሲሆን አመልካች ይህን ቤት በግዥ አላገኙትም፤ቤቱ በአዋጅ ያልተወረሰ ሲሆን ካርታ ሳይመክን አመልካች እኔም ካርታ አለኝ ሲል የሚያቀርበው ክርክር የህግ መሰረት የለውም የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንዲፀናልን ሲሉ ጠይቀዋል፡፡2ኛተጠሪ በበኩሏ በ21/08/2016ዓ.ም በሰጠችው ምላሽ ቤቱን ከ50 ዓመት በላይ ይዤ ስገለገልበት ቆይቻለሁ፤በመንግስት የኪራይ ሲስተም ውስጥ ተመዝግቦ የነበረ ነው፤የ1ኛ ተጠሪ ወራሾች በቤቱ ላይ ተገቢ መብት እንዳለቸው ማስረጃ ባላቀረቡበት አመልካች እና 2ኛ ተጠሪ ያስረክቡ በማለት መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፤የቤት ለውጡ ውል ባልፈረሰበት ሁኔታ ቀድሞ ያስረከብነው ቤት ይመለስልኝ በማለት ያቀረቡት ክስ በሰ/መ/ቁ/23331 የተሰጠውን አስገዳጅ ውሳኔ ይቃረናል፤በመሆኑም የስር የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ወስኖ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ያፀናው ውሳኔ እንዲሻር በማለት መልስ አቅርባለች፡፡አመልካች የሰበር አቤቱታውን የሚያጠናክር በ06/9/2016 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል ፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ያስቀርባል ሲባል የተያዘውን ጭብጥ ከግራቀኙ ክርክር፤በስር ፍርድ ቤት በማስረጃ ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር እና ከተገቢው የህግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡እንደመረመርነዉ የስር ከሳሾች የዳኝነት ጥያቄ በማካካሻነት የያዙት የመንግስት ቤት በልማት ምክንያት ስለፈረሰ የቀድሞ ቤታቸዉን ስር ተከሳሾች እንዲያስረክቡ እንዲወሰን የሚል ነዉ፡፡የስር ፍርድ ቤት የአመልካቹን ክርክር ዉድቅ አድርጎ ቤቱን እንዲያስረክብ ወስኗል፡፡ጉዳዩ ለሰበር ችሎት የቀረበዉ ተጠሪዎች በማካካሻነት የያዙት ቤት የሚገኝበት የቂርቆስ ክ/ከተማ አስተዳደር ወደ ክርክሩ እንዲገባ የተጠየቀዉ ዳኝነት የታለፈበትን አግባብ ለመመርመር ነዉ፡፡

በፍትሓብሄር ክርክር ተከሳሽ የሆነ ሰዉ በተከሰሰበት ነገር ዉስጥ ተካፋይ ያልሆነ ሌላ ሶስተኛ ወገን ከእኔ ጋር ድርሻ ካሳዉን መክፈል አለበት የሚል ሲሆን በክሱ ዉስጥ የሌለዉ ሶስተኛ ወገን በክሱ ዉስጥ የሚገባበትንና የድርሻዉን ልክ ጨምሮ በመግለጽ ወደ ክሱእንዲገባ ለመጠየቅ

ይችላል፡፡(የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 43(1) ይመለከቷል፡፡በዚህ አግባብ ሶስተኛ ወገን ወደ ክሱ እንዲገባለት ሲጠይቅ ከህግ ወይም ከዉል የመነጨ ግንኙነት መኖሩን ማሳየት ይጠበቅበታል፡፡ሶስተኛ ወገን ተከሳሽ ሆኖ የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆን የሚገደደዉ አንድም ከተከሳሽ ጋር ሃላፊነት ለመጋራት ወይም ሃላፊነትን ለመከላከል ሲሆን ይችላል፡፡በተያዘዉ ጉዳይ የቂርቆስ ክ/ከተማ አስተዳደር አካል ወደ ክርክሩ እንዲገባ የጠየቀዉ የአሁኑ አመልካች ሲሆን ለዚህም የጠቀሰዉ ምክንያት ለክርክር ምክንያት የሆነዉ ቤት የሚገኘዉ በዚሁ ክ/ከተማ በመሆኑና በልማት ምክንያት ያፈረሰዉም ይኸዉ ክ/ከተማ ስለሆነ ሃላፊነት እንዲወስድ በሚል መነሻ እንደሆነ ክርክሩ ያሣያል፡፡በመሰረቱ ግዴታ ወይም መብት የሚነጨዉ ከህግ ወይም ከዉል ነዉ፡፡በዚህም ጉዳይ ተጠሪዎች በማካካሻ (ለዉጥ) የያዙት ቤት የሚገኘዉ በቂርቆስ ክ/ከተማ አስተዳደር ስር እንደነበር ቤቱንም ያፈረሰዉ ይኸዉ ክ/ከተማ አስተዳደር መሆኑ ሲታይ ሃላፊነት ከህግ የመነጨ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡በሌላ በኩል ለስር ከሳሾች እንዲመለስ የተጠየቀዉ ቤት የሚገኘዉ በአመልካቹ አስተዳደር እጅ መሆኑም አላከራከረም፡፡ክሱ አመልካቹ ላይ የቀረበበት ምክንያትም ቤቱን ይዞ የሚገኘዉ አመልካቹ በመሆኑ እና የስር ፍርድ ቤት ለዉሳኔ መሰረት ያደረገዉ የቂርቆስ ክ/ከተማ አስተዳደር የሰጠዉ ማስረጃ ሲሆን ይዘቱም ሲታይ የተጠሪዎች አዉራሽ በማካካሻነት የያዙት የመንግስት ቤት በመልሶ ማልማት ምክንያት ስለፈረሰ የቀድሞ ቤታቸዉን እንዲታስረክቧቸዉ ተብሎ ለአመልካቹ የተጻፈ ደብዳቤ መሆኑን ያሣያል፡፡አመልካቹ ይህንን ለማስተባበል ያቀረበዉ ክርክርም ሆነ ማስረጃ የለም፡፡ይህ ከሆነ ደግሞ የቂርቆስ ክ/ከተማ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 4/2009 በሚፈቅደዉ አግባብ እንዲፈጸም ለአመልካቹ ስላስታወቀ ወደ ክርክሩ አለመግባቱ ከአመልካች ሃለፊነት አንጻር የሚያመጣዉ ለዉጥ የለም፡፡በዚህ ረገድ የስር ፍርድ ቤት ምክንያቱን በዉሳኔዉ ላይ አለመግለጹ ስህተት ቢሆንም የቂርቆስ ክ/ከተማ የክርክሩ ተካፋይ አለመደረጉ ከዉጤት አንጻር ሲታይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል የሚያሰኝ ሆኖ አላገኘነም፡፡

ሁለተኛዉ ማስቀረቢያ ጭብጥ በአመልካች እና በተጠሪዎች አዉራሽ መካከል የተደረገዉ የቤት ለዉጥ ዉል ሳይፈርስ ቤቱን አስረክብ መባሉን አግባብነት ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ/23331 ከሰጠዉ ገዥ ዉሳኔ አኳያ ለመመርመር ነዉ፡፡የአመልካቹ መከራከሪያ ለክርክር ምክንያት የሆነዉ ቤት በለዉጥ ዉል የተያዘ መሆኑ ስለተገለጸ የለዉጥ ዉል እንዲፈርስ ሳይደረግ ቤቱን ለማስለቀቅ የቀረበዉ ክስ ተቀባይነት የለዉም በማለት የተከራከረ ሲሆን ለዚህም ክርክር ማጣቀሻ ያደረገዉ ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ/ 23331 የሰጠዉን ዉሳኔ ሲሆን ተጠሪዎች በበኩላቸዉ ተጠቃሹ መዝገብ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የቤት ሽያጭ ዉል የሚመለከት መሆኑን ጠቅሰዉ ለተያዘዉ ክርክር አግባብነት እንደሌለዉ ተከራክረዋል፡፡

በእኛም በኩል ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ/23331 የሰጠዉን ዉሳኔ ይዘት እንደመረመርነዉ ክሱ ቤት ለማስለቀቅ የቀረበ ሲሆን ተከሳሽ ቤቱን የያዙት በሽያጭና ግዥ ዉል መሆኑን ጠቅሰዉ ስለተከራከሩ ሽያጭ ዉል መኖሩ ስላልተካደ ዉሉ ሳይፈርስ ቤቱን ለማስለቀቅ የቀረበዉ ክስ ተቀባይነት የለዉም ተብሎ የተወሰነ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች እና በተጠሪዎች አዉራሽ መካከል የነበረዉ ግንኙነት በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት የግል ቤት ለመንግስት አስረክቦ የመንግስትን ቤት በማካካሻነት ተረክቦ መጠቅም የሚቻልበት ሁኔታ በህግ የተፈቀደ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡ይሁንና ከመንግስት በመካካሻነት ወይም በለዉጥ የወሰዱት ቤት በመልሶ ማልማት ምክንያት የፈረሰ መሆኑን ከቂርቆስ ክ/ከተማ አስተዳደር መሬት ልማት ባንክና ከተማ ማደስ ፕሮጀክት ጽ/ቤት በቀረበ ማስረጃ የተረጋገጠ ፍሬነገር ጉዳይ ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ይዘት ያሣያል፡፡እንዲህ በሆነ ጊዜ ደግሞ ለባለመብቱ የቀድሞ ቤት እንዲመለስለት የሚደረግ ስለመሆኑ በመመሪያ ቁጥር 4/2009 በግልጽ የተደነገገ ስለመሆኑ እና የስር ፍርድ ቤትም ይህንኑ መሰረት በማድረግ ዉሳኔ መስጠቱን ተገንዝበናል፡፡ በዚህ መመሪያ አተገባበር ረገድ የተፈጸመ ስህተት ስለመኖሩ የሚያሣይ ቅሬታ አልቀረበም፡፡ስለሆነም ተጠሪዎች ከመንግስት የወሰዱት ቤት የመገልገል መብት የተቋረጠዉ ቤቱ ለመልሶ ማልማት ስለፈረሰ መሆኑን እና ለዚህም በህግ የተቀመጠዉ መፍትሄ የቀድሞ ቤት እንዲመለስላቸዉ ማድረግ ነዉ፡፡በመሆኑም የቀድሞ ዉል አልፈረሰም የሚለዉ ክርክርም ሆነ ተጠቃሹ የሰበር ችሎት ዉሳኔ ለተያዘዉ ክርክር አግባብነት የለዉም ብለናል፡፡ስለሆነም በዚህ ረገድ አመልካቹ ያቀረበዉ ክርክር በስር ፍርድ ቤት ዉድቅ መደረጉ የሚነቀፍበት ምክንያት የለም፡፡

ሲጠቃለል ለክርክር ምክንያት የሆነዉ ቤት ለስር ከሳሾች እንዲመለስ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ በማስረጃ የተደገፈ እና አግባብነት ያለዉን ህግ መሰረት ያደረገ መሆኑን በመገንዘብ የስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ከዉጤት አኳያ ሲታይ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 መሰረት በዚህ ሰበር ችሎት ሊታረም የሚገባ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል የሚያሠኝ ምክንያት አልተገኘም፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

## ዉሳኔ

1ኛ/የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/50994 ላይ በቀን 16/05/2015ዓ.ም የሰጠዉ ፍርድ እና ይህንኑ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 303595 ላይ በቀን 19/08/2015ዓ.ም የሰጠዉ ትእዛዝ በሰበር ስነስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1) መሰረት ጸንቷል፡፡

2ኛ/በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በግራ ቀኙ የወጣ ወጪ ካለ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል

**መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁጥር 248162

ጥቅምት 07 ቀን 2017 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

ሰናይት አድነው

ሀፊዝ አባጀማል

**አመልካች፡-** አቶ ኃይሉ አበራ ቀዌ -ቀርበዋል

**ተጠሪዎች፡-** 1.ቢ.ቲ.ኤም ጠቅላላ የቤትና የቢሮ እቃዎች አምራች ኃ/የተ/የግ/ማህበር ሥ/አስኪያጅ ብርሃኑ ዳኛቸው ቀርበዋል

2. አቶ ብርሃኑ ዳኛቸው ይመር -ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች በተጠሪዎች ላይ ያቀረበዉን ክስ መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡ የአመልከች ክስ ይዘትም በአጭሩ 2ኛ ተጠሪ የድርጅቱ ስራ አስኪያጅ እና ባለቤት ሲሆን በ1ኛ ተጠሪ ስም ለኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የተለያዩ የቢሮ እቃዎችን ሰርቶ ለማቅረብ እንዲያስችለው ከአመልካች ከወሰደው ገንዘብ እና የእቃዎች ክፍያ የሚሆን ቼክ በ2ኛ ተጠሪ ፈራሚነት በተለያየ ጊዜ እየሰጠኝ ጊዜው ሲደርስ እያደሰ በመጨረሻም ለክፍያ ብር 1,000,000.00 የያዘ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የወጣ ቁጥሩ ጂ.ኢ.ኤች 11088454 የሆነ ቼክ በነሀሴ 12 ቀን 2012 ዓ.ም ሰጥዉኝ ቼኩን ለመመንዘር ወደ ባንክ ስሄድ በቂ ስንቅ እንደሌለዉ የተገለጸለት መሆኑን ጠቅሶ ተጠሪዎች በቼኩ ላይ የተመለከተዉን ገንዘብ መክፈል ከነበረበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍሉኝ ይወሰንልኝ የሚል ነዉ፡፡

ተጠሪዎች በሰጡት መልስ አመልካች በክሳቸው የጠቀሱት ብር 1,000,000 ለስራ ማስኬጃ እንዲሆን እና ዩኒቨርሲቲው ክፍያውን እንደፈፀመ ሊመልስላቸው ሚያዚያ 22 ቀን 2010 ዓ.ም በተደረገ የገንዘብ ብድር ውል በፍላጎታቸው ተስማምተው ብድር የሰጡ ሲሆን በተጨማሪም ለዚሁ ብር መተማመኛ እንዲሆን ጥር 18 ቀን 2011 ዓ.ም ዩኒቨርሲቲው የተሰራለትን እቃ ተረክቦ ክፍያውን ባለመፈፀሙ ምክንያት ጉዳዩ በመዝገብ ቁጥር 227849 እየታየ በመሆኑ ክርክሩ ውሳኔ አግኝቶ ገንዘብ እስኪከፈል ድረስ የማይመነዘር የቼክ መተማመኛ በየ6 ወሩ የሚቀየር በአመልካች ስም እየተዘጋጀ ሊሰጣቸው ስምምነት የተደረገ ስለመሆኑ የቼክ መተማመኛ ውሉ በግልጽ የሚያሳይ ሆኖ እያለ አመልካች እራሳቸው በፍቃደኝነት እና በስምምነት የተዋዋሉትን በመካድ እና ምንም አይነት ስምምነት እና ውል እንዳልተፈፀመ በማስመሰል በሀሰት ያቀረቡት ክስ ስለሆነ ክስ ውድቅ እንዲሆን በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ተጠሪዎች ለቼኩ መሰጠት መነሻ የሆነው ከአመልካች ጋር ባላቸዉ ግንኙነት መነሻነት መሆኑን ጠቅሰዉ ለዚህም የተለያዩ ውሎችን በማስረጃነት ማቅረባቸዉን፤ አንደኛዉ ዉል ሚያዚያ 15 ቀን 2010 ዓ.ም የተደረገ የስራ ውል ሲሆን ዉሉ 1ኛ ተጠሪ ከአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ እና ከኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ጋር ጠረጴዛዎችን እና የመምህራን አልጋ ለመስራት በተደረገዉ ውል መሰረት አመልካች ባላቸው የስራ ልምድ በራሳቸው ወጪ ስራውን እንዲሰሩ እና ከስራው ከሚገኘው ገቢ ለመካፈል መስማማታቸዉንና ክፍያውም ዩኒቨርሲቲው ስራውን ተረክቦ ክፍያ ሲፈጽም የሚከፈል መሆኑን የሚያሳይ ቢሆንም በውሉ ላይ የተገለፀ የገንዘብ መጠን አለመኖሩን፤ በሚያዚያ 22 ቀን 2010 ተደርጓል በሚል የተገለጸዉ እና አመልካች ያመነው የብድር ውል 1ኛ ተጠሪ ድርጅት ከኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ላሸነፈው የፈርኒቸር ስራ ማስኬጃ የሚሆን ብር 1,000,000.00 አመልካች መስጠቱን እና ተጠሪዎችም ይህንን ገንዘብ ዩኒቨርሲቲው ሲከፍላቸው የሚመለስ መሆኑን ተገልፆ በጥር 18 ቀን 2011 ዓ.ም የቼክ መተማመኛ ዉል መደረጉን፤ የሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ክፍያውን ባለመፈጸሙ ጉዳዩ ወደ ፍርድ ቤት በመውሰድ ለአመልካች በየስድስት ወሩ የሚቀየር ቼክ ተጠሪዎች ለመስጠት መስማማታቸውን የሚገልጽ መሆኑን፤ ይሁንና አመልካች ጥር 18 ቀን 2011 ዓ.ም እና ሚያዚያ 15 ቀን 2010 ዓ.ም የተፈፀሙት ውሎችን እንደማያውቃቸው ክደው መከራከራቸዉን ተከትሎ በተጠሪዎች የቀረቡት ምስክሮች ቀርበዉ ዉሎቹ መደረጋቸዉን የመሰከሩ ቢሆንም በዉሎቹ ላይ የተመለከተዉ ፊርማ የአመልካች አለመሆኑን በፎረንሲክ ምርመራ መረጋገጡንና ይህም ዉሎቹ እንዳልተደረጉ አመላካች መሆኑን፤ በአጠቃላይ ተጠሪዎች ለቼኩ መሰጠት መነሻ ነዉ ያሉት የግል ግንኙነት ስለመኖሩ የንግድ ህጉ አንቀጽ 717 በሚጠይቀዉ አግባብ አላስረዱም በማለት በቼኩ ላይ የተመለከተውን ብር 1,000,000.00 ተጠሪዎች ከመስከረም 12 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር በአንድነት እና በነጠላ እንዲከፍሉ በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪዎች በዚህ ውሳኔ ባለመስማማት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን፣ ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት በበኩሉ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቼክ ለአመልካች የተሰጠው ተጠሪዎች ከኢትዩጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ጋር በገቡት ውል መሰረት ለውል ምክንያት የሆኑ 260 አልጋዎችን አመልካች ሰርተው ከዩኒቨርሲቲው ክፍያ ሲፈፀም በቼኩ ላይ የተመለከተውን ገንዘብ ለመክፈል መሆኑን፣ ነገር ግን 260 አልጋዎች በተገባው ውል መሰረት ባለመሰራታቸው ክፍያው ለተጠሪዎች አለመከፈሉ በመረጋገጡ ተጠሪዎች ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ቼክ ላይ የተመለከተው ገንዘብ ከወለዱ ጋር ለአመልካች ሊከፈል አይገባም በማለት የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤቱን ዉሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች ግንቦት 28 ቀን 2015 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተፈጽመዋል ያለዉን ስህተት በመዘርዘር በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸዉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአቤቱታቸው ይዘትም በአጭሩ ተጠሪዎች ለክፍያ ቼክ መስጠታቸውን ሳይክዱ በቼክ ከሚመጣባቸው ኃላፊነት ለመዳን በሀሰት ያዘጋጁት የውል ሰነዶች በፎሬንሲክ ምርመራ በአመልካች ያልተፈረመ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ 2ኛ ተጠሪ ባቀረበው ሰነዶች ላይ የራሱን ጓደኞች ብቻ ምስክር አድርጎ ማስፈረሙ አስቀድሞውኑ በሀሰተኛ ሰነድ ለመጠቀም አቅዶ የሰራ መሆኑ ያመለክታል፡፡ በዚሁ ጉዳይ ቀርበው እንዲመሰክሩ የተደረጉት የተጠሪ ምስክሮች ብቻ ሆኖ እያለ እና ሰነዱ በፎረንሲክ ተመርምሮ በአመልካች አለመፈረሙ እስከተረጋገጠ ድረስ በሀሰተኛ ሰነድ ላይ የፈረሙ ምስክሮችን ቃል መስማት የፎረንሲክ ምርመራ ውጤት አልባ የሚያደርግ ሀሰተኝነትን የሚያበረታታ በመሆኑ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገቡ ላይ የአመልካች ምስክር ሳይሰማ በሀሰተኛ ሰነድ ላይ በምስክርነት የተመዘገቡትን የተጠሪ ምስክሮች ቃል ብቻ መሰረት በማድረግ ክሴን ውድቅ ማድረጉ የህግ ስህተት ስለሆነ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሮ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲፀናልኝ የሚል ነው፡፡

የሰበር አቤቱታዉ በዚህ ችሎት ተመርምሮም ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በቼክ ላይ የተመለከተው ገንዘብ ለአመልካች ሊከፈል አይገባም በማለት የስር ፍ/ቤት ያሳለፈውን ውሳኔ የሻረው የግራ ቀኙን ክርክር በአግባቡ በመመርመር እና ለውሳኔውም በቂ ምክንያ በመስጠት መሆን አለመሆኑን አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል ተብሏል፡፡ በዚሁም መሠረት ተጠሪዎች መጋቢት 17 ቀን 2016 ዓ.ም በተፃፈ መልስ በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ የሰበር ውሳኔ እና የህግ አተረጓጎም መርሆችን እንዲሁም የቀረቡ ማስረጃዎችን በአግባቡ ሳያገናዝብ በመካከላችን በነበረዉ የስራ ግንኙነት መሠረት አመልካች ግዴታዉን ሳይወጣ እና በስራዉ መሠረት የተከፈለን ገንዘብ ሳይኖር ገንዘቡን እንድንከፍል የሰጠዉን ዉሳኔ በመሻር የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ በበቂ ምክንያት የተደገፈ በመሆኑ የህግ ግድፈት የለበትም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዉ ተከራክረዋል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል፣ ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነዉን ዉሳኔ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግበባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደሚቻለዉ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ለጠየቀዉ ዳኝነት መሠረት ያደረጉት ተጠሪዎች ለብድር ዕዳ መመለሻ እንዲሆን በሚል የሰጧቸዉ የ1000,000.00 ብር ቼክ ስንቅ የሌለዉ በመሆኑ ገንዘቡን የመክፈል ኃላፊነት ያለባቸዉ መሆኑን ሲሆን፣ ተጠሪዎች በበኩላቸዉ ተጠሪዎች ከኢትዮጵያ ስቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ በጨረታ ያሸነፉትን ስራ አመልካች ሰርተዉ ትርፍ ለመካፈል ተስማምተዉ ለዚሁ ስራ ማስከጃ እንዲሆን ብር 1000,000.00 አመልካች የሰጣቸዉ መሆኑን፣ ይሁንና ገንዘቡ የሚከፈለዉ ዩኒቨርሲቲዉ ለተሰራ ስራ ክፍያ ሲፈጽም ስለመሆኑ ተስማምተዉ ዩኒቨርሲቲዉ የተሰራለትን ዕቃ ተረክቦ ገንዘቡን እስከሚከፍል ድረስ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቼክ ለመተማመኛ ለአመልካች የሰጡት መሆኑን ጠቅሰዉ ተከራክረዋል፡፡ ክርክሩ ቼክን የሚመለከት ሲሆን፣ ቼኩ የተሰጠዉ በተጠሪዎች ስለመሆኑ አላከራከረም፡፡ ስለሆነም ተጠሪዎች ከኃላፊነት ነፃ ሊሆኑ የሚችሉት በ1952 ዓ.ም በወጣዉ የኢትዮጵያ የንግድ ህግ አንቀጽ 717 ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች አንዱን በመጥቀስ ከተከራከሩ እና ክርክራቸዉም ተቀባይነት ሲያገኝ ነዉ፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት ለመከላከያነት

ከሚቀርቡ መከራከሪያዎች ዉስጥ አንዱ ለቼኩ መሰጠት ምክንያቱ በቼክ አዉጪዉና ተቀባዩ መካከል የነበረ የግል ግንኙነት ስለመሆኑ በድንጋጌዉ ንዑስ ቁጥር 1 ላይ ከተመለከተዉ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የተጠሪዎች ክርክርም ይህንኑ መሠረት ያደረገ ነዉ፡፡ በመሆኑም በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 246(1) መሠረት በጉዳዩ ላይ ፍትሐዊ ዉሳኔ ለመስጠት መያዝ የሚገባዉ ትክክለኛ ጭብጥ *"ቼኩ የተሰጠዉ የኢትዮጵያ ስቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ላሰራዉ ስራ ክፍያ ሲፈጽም ተጠሪዎች ለአመልካች ብር 1000,000.00 ለመክፈል ስምምነት ነዉ ወይስ ለክፍያ ነዉ?"* የሚል ነዉ፡፡ የስር ሁለቱም ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን በዚህ አግባብ በመመርመር በተለያየ ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል፡፡ ከላይ እንደተገለጸዉ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ለቼኩ መሰጠት ምክንያቱ በግራ ቀኛቸዉ የተፈጠረ የግል ግንኙነት መኖሩን አላስረዱም በሚል የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ የደረሰ ሲሆን፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በበኩሉ ለቼኩ መሰጠት ምክንያቱ ተጠሪዎች ከዩኒቨርሲቲዉ ጋር ያደረጉትን ስራ አመልካች ሰርተዉ ክፍያዉ ሲከፈላቸዉ በቼኩ ላይ የተመለከተዉን ገንዘብ ለመክፈል በተገባዉ ስምምነት ስለመሆኑ ተረጋግጧል በሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ ተጠሪዎች ኃላፊነት የለባቸዉም በማለት ወስኗል፡፡

እንግዲህ ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት ከመሆኑ አኳያ፣ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሻ ጭብጥ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ የተፈጸመ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩ ነዉ፡፡ እንደሚታወቀዉ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80 (3/ሀ) ላይ በግልጽ እንደተመለከተዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉን ዉሳኔዎች በማረም ላይ የተገደበ ነዉ፡፡ *መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት ነዉ? ወይም አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ መቼ ነዉ?* የሚለዉን ጽንሰ ሃሳብ አስመልክቶ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 *መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት* እንደሆነ ትርጓሜ ይሰጣል፡፡ በአዋጁ በትርጉም ክፍል አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለዉ አንድ ዉሳኔ *መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን፣ ህግ ያላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉን ህግ የሚጠቅስ፣ ለክርክሩ አግባብነት ያለዉ ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለዉ ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፣ በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ዉድቅ በማድረግ የተወሰነ፣ በፍርድ አፈፃፀም ሂደት ከዋናዉ ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትዕዛዝ የተሰጠበት፣ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተወሰነ፣ የአስተዳደር አካል ወይም ተቋም ከህግ ዉጭ የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ በመቃረን የተወሰነ ሲሆን ነዉ፡፡*

ከዚህ አንፃር የተያዘዉን ጉዳይ ስንመለከት፣ ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቀረቡትን ማስረጃዎች መርምሮ የስር ፍርድ ቤት የደረሰበትን የፍሬ ነገር ድምዳሜ ለዉጦታል፡፡ ለዚህ ዉሳኔዉ በማስረጃ ረገድ የሰጠዉ ትንታኔም ተጠሪዎች ካቀረቧቸዉ ዉሎች አንደኛዉ እና በአመልካች የተካደዉ ሚያዝያ 15 ቀን 2010 ዓ.ም ተደረገ የተባለዉ ሲሆን፣ የዉሉ ይዘትም ተጠሪዎች ከአዳማ ዩኒቨርሲቲ እና ከኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ጋር ጠሬጴዛዎችንና የመምህራንን አልጋ ለመስራት በፈጸሙት መሰረት አመልካች ባላቸው የስራ ልምድ በራሳቸው ወጪ ስራውን እና ከስራው የሚገኘውን ገቢ ለመካፈል ከዩኒቨርሲቲው ጋር የተደረገውን ውል አባሪ በማድረግ የውል ስምምነት

**ማስታወሻ፡** - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

የገቡ መሆኑን እንደሚያሳይ፤ ተጠሪዎች በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ጋር በነበራቸው ክርክር አመልካች ለተጠሪዎች ምስክር ሆነው ቀርበው ለክርክር ምክንያት የሆኑትን 260 አልጋዎች አመልካች ሰርተው ለዩኒቨርሲቲው ያስረከቡ መሆኑን በመግለጽ የመሰከሩ መሆኑን፣ ሆኖም እነዚህ አልጋዎች በውሉ መሰረት ባለመሰራታቸው በተጠሪዎች የተጠየቀው ክፍያ ከዩኒቨርሲቲው ሊከፈላቸው አይገባም በማለት የተወሰነ መሆኑን ከፌ/ከ/ፍ/ቤት መ/ቁ 227849 መዝገብ መረዳቱን፤ ለቼኩ መሰጠት ምክንያቱ ተጠሪዎች ከዩኒቨርሲቲው ጋር ያደረጉትን ስራ አመልካች ሰርተው ክፍያው ሲከፈላቸው በቼኩ ላይ የተመለከተውን ገንዘብ ለአመልካች ለመክፈል በተገባው ስምምነት መሰረት መሆኑን በስር ፍ/ቤት የቀረቡት ምስክሮች ማስረዳታቸዉን፤ በዉሉ ላይ የተመለከተዉ ፊርማ በአመልካች ያልተፈረመ መሆኑ በፎረንሲክ ምርመራ ቢረጋገጥም በስር ፍርድ ቤት የቀረቡት ምስክሮች እና በተጠቃሹ መዝገብ ላይ የተሰጠ ዉሳኔ በአጠቃላይ ሲታይ አመልካች ለቼኩ መሰጠት ምክንያቱ ከዩኒቨርሲቲዉ ክፍያ ሲፈጸምላቸዉ ገንዘቡን ለመክፈል የተገባዉ ስምምነት ስለመሆኑ ተረጋግጧል የሚል ይዘት ያለዉ ነዉ፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዚህ ሁኔታ ማስረጃዎችን መርምሮ እና መዝኖ በመወሰን ሂደት የፈጸመዉ የማስረጃ አቀባበል እና የምዘና መርህ ስህተት ስለመኖሩ የዉሳኔዉ ይዘት አያሳይም፡፡ ሚያዝያ 15 ቀን 2010 ዓ.ም ተደርጓል በተባለዉ ላይ የተፈረመዉ ፊርማ የአመልካች አለመሆኑ በፌዴራል ፖሊስ የፎረንሲክ ምርመራ የተረጋገጠ ቢሆንም፣ ፍርድ ቤቱ የመረመራቸዉ ሌሎች ማስረጃዎች ተጠሪዎች ከተጠቀሱት ዩኒቨርሲዎች ጋር ያደረጉትን ጠረጴዛዎችንና የመምህራን አልጋ ለመስራት የገቡትን ግዴታ አመልካች ባላቸዉ የስራ ልምድ በእራሳቸዉ ወጪ ሰርተዉ ከስራዉ የሚገኘዉን ገቢ ለመካፈል መስማማታቸዉንና ቼኩ የተሰጠዉም በዚሁ መነሻነት ሆኖ ነገር ዩኒቨርሲቲዉ ለተጠሪዎች ክፍያ ያልፈጸመ መሆኑን እስካስረዱ ድረስ ፊርማዉ የአመልካች አለመሆኑ መረጋገጡ ብቻዉን ይህ ግንኙነት የለም ከሚል የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ አያደርስም፡፡ የሙያ ማስረጃ ብቻዉን እምነት እንደማይጣልበት እና አግባብነት ባለዉ ሌላ ማስረጃ ሊስተባበል እንደሚችል የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰ/መ/ቁ 43453 ጨምሮ በሌሎች በርካታ መዛግብት ላይ የሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም ልብ ይሏል፡፡

ከዚህ ሁሉ አንፃር ሲታይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ዉሳኔ በመሻር በቼኩ መነሻነት ለተጠየቁት ክፍያ ተጠሪዎች ኃላፊነት የለባቸዉም በማለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ የተፈጸመ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ዉሳኔ**

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 229866 ላይ የካቲት 29 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1) መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ዉሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

የሰ/መ/ቁጥር 248287

ጥቅምት 08 ቀን 2017 ዓ/ም

ዳኞች፡-እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች፡- መምህር ሲራክ ተረፈ - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. ወ/ሮ ሀረጓ ዳዲ - አልቀረቡም

2ኛ. አቶ መካ መሀዲ - አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ በዳኞች የእረፍት ጊዜ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

# ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች በ29/09/2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የሀረሪ ክልል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 22551 በ30/06/2014 ዓ.ም የሰጠውን ብይን የሀረሪ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 06062 በ30/09/2014 ዓ.ም በማፅናት መወሰኑ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለታቸው ሲሆን በስር ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ከሳሽ ሆነው ተጠሪዎች ተከሳሾች ሆነው በውርስ ድርሻ ጉዳይ ተከራክረዋል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አመልካች በስር ፍ/ቤት በቀን 27/03/2014 ዓ/ም ባቀረቡት የክስ አቤቱታ በሐረር ከተማ ቀበሌ 16 የቤ/ቁጥር 452 የሆነ በ700 ካ/ሜ ላይ ያረፈ በሟች አባቴ ተረፈ ተሰማ ስም የተመዘገበ የመኖሪያ ቤት ያለ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ (የእንጀራ እናቴ) ከሌሎች 3 የሟች ተወላጆች (ወራሾች) ጋር ቤቱን በብር 2,672,000.00 ለ2ኛ ተጠሪ ሸጠው የውርስ ሀብቱን የተከፋፈሉ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ የሚስትነት ድርሻቸዋን ግማሹን የወሰዱ ሲሆን ቀሪው ግማሹ ድርሻ የሟች አባታችን በመሆኑ የሟች ተወላጆች የሆኑት 3ቱ ወራሾች እያንዳዳቸው ብር 334,000.00 (ሶስት መቶ ሰላሳ አራት ሺ ብር) የወሰዱ በመሆኑና እኔ ግን ድርሻዬን ያልሰጡኝ በመሆኑ የውርስ ድርሻዬን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በጋራም ሆነ በተናጠል ከወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፍሉኝ ይወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

1ኛ ተጠሪ በህጉ አግባብ ጥሪ ቢደረግላቸውም መልሳቸውን ያላቀረቡ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ በ28/4/14 ዓ/ም ምላሽ የሰጡ ሲሆን ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት በህጋዊ መንገድ በሽያጭ ተላልፎልኝ ስመ ሀብቱም በስሜ የተመዘገበና በስሜ ግብር የምገብርበት በመሆኑ ክሱ ደግሞ የውርስ ክፍፍል ድርሻዬ አልተከፈለኝም የሚል በመሆኑ ክሱ አይመለከተኝም፤አመልካች ያቀረቡት ክስ ቤቱ መቼ እንደተሸጠ እንኳን የማይገልፅ በመሆኑ ክሱ ግልፅነት የጎደለውና የመከላከል መብቴን የሚያጣብብ በመሆኑ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል ፤ የአመልካች ክስ የውርስ ድርሻዬ ይከፈኝ የሚል በመሆኑ እኔ ግን ቤቱን የገዛሁት በህጋዊ መንገድ በመሆኑ አመልካች ድርሻቸውን ሊጠይቁ የሚችሉት ከሌሎች ወራሾች በመሆኑ ከ2ኛ ተጠሪ ላይ ሊጠይቁ የሚችሉት መብትና ጥቅም የለም ተብሎ ክሱ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ በሰጠው ብይንም አመልካች ያቀረቡት ክስ የሽያጭ ውሉ የተደረገበትን ቀን የማያመለክት ግልፅነት የጎደለው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ 1ኛ ተጠሪ ከሟች በጋራ ያፈሩትን ቤት ከሌሎች የሟች ተወላጆች ጋር በመሆን ሸጠው የሚስትነት ድርሻቸውን የወሰዱ ሲሆን ቀሪው ግማሽ ድርሻ የሟች እንደመሆኑ መጠን አመልካች ድርሻቸውን ሊጠይቁ የሚችሉት ከወንድሞቻቸው ላይ እንጂ ከ2ኛ ተጠሪ ላይ ባለመሆኑ በ2ኛ ተጠሪ ላይ ክስ የማቅረብ መብትና ጥቅም የላቸውም በማለት ክሱን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.33 መሰረት ውድቅ አድርጎታል፡፡ይህ ብይን በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ፀንቷል፡፡አመልካች በዚህ ትዕዛዝ ቅር ተሰኝተው የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ቢሆንም ግራ ቀኙ በተለያየ ክልል ነዋሪ በመሆናቸው ጉዳዩን በሰበር የማየት ስልጣን የለኝም በማለት የሰበር አቤቱታውን ሰርዞታል፡፡

አመልካችም የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት በ29/09/2015 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ለዚህ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፦ የአባቴን ቤት ያለ እኔ ፊርማ የገዛው ሁለተኛ ተጠሪ በደቡብ በኩል ቤቱን የሚያዋስን እና እኔንም ሆነ

ሟች አባቴንም በጉርብትና የሚያውቀን ከመሆኑም በላይ ከአባቴ ሞት በኋላ በመምህርነት ስራ ተቀጥሬ ስራዬ ደደር ቢሆንም በየሳምንት እየመጣሁ የማርፍበት ቤታችን መሆኑን እያወቀ ስለእኔ ስምምነትና ፊርማ ሳይፈልግ ግገር መፈፀሙ የሽያጭ ውሉን ፈራሽ የሚያደርግ መሆኑን፤አንደኛ ተጠሪ ከቤቱ የሚስትነት ድርሻ በፍ/ቤት አስወስና በራሷ ድርሻ ግብር የከፈለችበት ወይም በስሟ ካርታ ያሰራችበት ማስረጃ በትእዛዝ ሳይቀርብ በጥቅሉ የወራሾች ድርሻ ያለበት ንብረት ከእሷ የሚወለዱ ወንድሞቼ ጋር ስምምነት አድርጋ የእኔ ድርሻ ጭምር የሸጠችበትን ሰነድ ፍርድ ቤቱ በህጋዊነት ተቀብሎ የቤቱ ሽያጭ ድርሻ ወንድሞቹን ይጠይቅ በማለት መወሰኑ ኢ-ፍትሃዊ ውሳኔ ከመሆኑም በዘለለ የህግ ጥሰት የተፈፀመበት ውሳኔና ትእዛዝ ስለሆነ የአንድ የውርስ ንብረት ተጋሪ እያለ በሽያጩ ሂደት ፈቃደኝነት ወይም ስምምነት እንዲሁም ፊርማው ሳይኖር የተፈፀመን ህገወጥ ሽያጭ ውል መሰረት በማድረግ መወሰኑ አግባብ ባለመሆኑ የሽያጭ ውሉ ፈርሶ ቤቱን እንዲያስረክበኝ፤ ቤቱን እፈልጋለሁ የሚል ከሆነም ድርሻዬን ብር 334,000.00 ለአንደኛ ተጠሪም ሆነ ለወንድሞቼ በድርሻቸው ላይ ደርቦ የሰጠበት ማስረጃ የሌለው ስለሆነ ድርሻዬን ብር 334,000.00 ከወጪና ጉልበት ኪሳራ ጭምር ታስቦ ንዲከፈለኝ እንዲወሰንልኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

አቤቱታው የቀረበለት የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ለዚህ ችሎት ከመራው በኋላ ይህ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ፦ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ክሳቸውን ያቀረቡት በሁለቱም ተጠሪዎች ላይ ሆኖ እያለ አመልካች በ1ኛ ተጠሪ ላይ ያቀረቡትን ክስ በተመለከተ ዳኝነት ሳይሰጥ የማለፉ አግባብነት ሊመረመር የሚገባው በመሆኑ ተጠሪዎች መልስ ይስጡበት በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ መጥሪያ እንዲያደርሱ ቢታዘዝም መጥሪያ ለማድረሳቸው ማረጋገጫ አለማቅረባቸው መጥሪያው ለ1ኛ ተጠሪ ያልደረሰው በአመልካች ጉድለት መሆኑን የሚያሳይ መሆኑን በመጥቀስ አመልካች በ1ኛ ተጠሪ ላይ ያቀረቡትን የሰበር ቅሬታ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.199 መሰረት ሰርዞታል፡፡

2ኛ ተጠሪ በ01/08/2016 ዓ.ም የተጻፈ መልስ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፦ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 27(3) መሰረት ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሚቀርብ የሰበር አቤቱታ የመጨረሻ የፍርድ ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በ90 (ዘጠና) ቀናት ውስጥ መቅረብ እንዳለበት በግልፅ ተደንግጓል፡፡ የሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የመጨረሻ ትዕዛዝ የሰጠው በቀን 21/06/2015 ዓ.ም ሲሆን አመልካች ለዚህ ፍርድ ቤት አቤቱታውን ያቀረበው ደግሞ በቀን 29/9/2015 ዓ.ም ነው፡፡ አቤቱታው መቅረብ በነበረበት የዘጠና ቀን ሳይቀርብ ስምንት (8) ቀናት ዘግይቶ የሰበር አቤቱታው የቀረበ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 27(3) አቤቱታው ውድቅ ሊደረግ ይገባል፤የሰበር አቤቱታው በስር ፍርድ ቤቶች የተፈፀመን መሰረታዊ የህግ ስህተት ከማሳየት ይልቅ በፍሬ ነገር ላይ የቀረበ በመሆኑ የሰበር አቤቱታው ውድቅ ሊደረግ ይገባል፤ አመልካች ክርክር ባቀረበበት ቤት ላይ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ምንም ዓይነት መብት የለውም፡፡ ክርክር የቀረበበት ቤት የአንደኛ ተጠሪ የግል ንብረት ነው፡፡ የአመልካች አባት ከአንደኛ ተጠሪ ጋር በጋብቻ ወቅት ያፈራው የጋራ ንብረት ባለመሆኑ አመልካች በዚህ ቤት ላይ ምንም ዓይነት የወራሽነት መብት የለውም፡፡ የፌደራል ጠ/ፍ/ቤት/ሰ/ሰ/ችሎት በሰ/መ/ቁ.47378 ቅፅ 10 ላይ በሰጠው ውሳኔ ላይ ከውርስ ጋር በተያያዘ በቤት ሽያጭ ላይ ገዥው ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጎ ግዢውን እስኪፈፀም ድረስ መብት አለኝ የሚለው ወገን ጥያቄ ማቅረብ የሚችለው ከሻጭ እንጂ ከገዢ ላይ አለመሆኑን በማመልከት አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሰጠ በመሆኑ፣ 2ኛ ተጠሪ እና አንደኛ ተጠሪ ያደረግነው የቤት ሽጭ ውል ህጋዊ ሲሆን የሐረሪ ክልል ከተማ ልማት ለአመልካች የቤት ካርታ ደንቡን ጠብቆ የሰጠኝ በመሆኑና ካርታውን ለማምከን የሚያስችል ምንም ዓይነት ምክንያት ያልቀረበ በመሆኑ እንዲሁም ተጠሪ በፈፀምነው የቤት ሽያጭ ውል መሰረት የቤቱን ሽያጭ ዋጋ ለሻጭ በተገቢው ጊዜ የፈፀምኩ በመሆኑ በድጋሚ ለአመልካች ብር 334,000 (ሶስት መቶ ሰላሳ አራት ሺህ ብር) የምከፍልበት የፍሬ ነገርም ሆነ የህግ መሰረት ባለመኖሩ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካችም ለ2ኛ ተጠሪ መልስ በ29/08/2016 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ አቤቱታቸውን አጠናክረዋል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተነው ሲሆን እኛም ያስቀርባል ሲባል የተያዘውን ጭብጥ ከግራቀኙ ክርክር፣ በስር ፍርድ ቤት ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች እና ከተገቢው ህግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር መርምረን እንደተረዳነዉ በዚህ ችሎት የማስቀረቢያ ነጥብ ሆኖ የተያዘዉና የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሻዉ ጭብጥ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ክሳቸውን ያቀረቡት በሁለቱም ተጠሪዎች ላይ ሆኖ እያለ አመልካች በ1ኛ ተጠሪ ላይ ያቀረቡትን ክስ በተመለከተ ዳኝነት ሳይሰጥ ማለፉ አግባብ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ቢሆንም ከላይ እንደተመለከተው አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ መጥሪያ እንዲያደርሱ ቢታዘዝም መጥሪያ ለማድረሳቸው ማረጋገጫ አለማቅረባቸው መጥሪያው ለ1ኛ ተጠሪ ያልደረሰው በአመልካች ጉድለት መሆኑን የሚያሳይ መሆኑን በመጥቀስ አመልካች በ1ኛ ተጠሪ ላይ ያቀረቡትን የሰበር ቅሬታ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.199 መሰረት ችሎቱ የሰረዘው በመሆኑ በችሎቱ በተያዘው የማስቀረቢያ ጭብጥ ላይ ተገቢው ፍርድ የሚሰጥበት አግባብ ባለመኖሩ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## <u>ውሳኔ</u>

1.አመልካች በ1ኛ ተጠሪ ላይ ያቀረቡትን የሰበር ቅሬታ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሚያዚያ 29 ቀን 2016 ዓም በዋለው ችሎት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.199 መሰረት የሰረዘው በመሆኑ፣ይህም ከማስቀረቢያ ነጥቡ አንፃር

<u>ማስታወሻ</u>፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሚመረመር ነጥብ አለመኖሩን ስለሚያሳይ የሰበር አቤቱታው ውድቅ ተደርጓል፡፡

2.አመልካችና 2ኛ ተጠሪ በሰበር ክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

**<u>ጉዳዩ ውሳኔ ስላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡</u>**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁጥር248362

ጥቅምት 05 ቀን 2017 ዓ.ም

**ዳኞች፡-**ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻዉ አዳነ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሠናይት አድነዉ

ሀፊዝ አባጀማል

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ጫልቱ ዋቅጋሪ

**ተጠሪ፡-** ሰሚት ኢንጂነሪንግ ፕላስቲክ ፋብሪካ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር ነ/ፈ ተሾመ በሱፈቃድ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ አፈፃፀምን የሚመለከት ሲሆን፣ የተጀመረዉም በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነዉ፡፡ የጉዳዩም መነሻ ተቀጥረዉ ሲሰሩበት ከነበረዉ ከስቶር ጸሐፊነት የስራ መደብ ተጠሪ ከህግ ዉጪ ከስራ ያሰናበቷቸዉ መሆኑን ጠቅሰዉ አመልካች ያቀረቡትን ክስ መሠረት በማድረግ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 133619 ላይ ህዳር 20 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት ስንብቱ ህገ ወጥ መሆኑን ጠቅሶ ተጠሪ አመልካችን ወደ ስራ መደባቸዉ እንዲመልስ ዉሳኔ ሰጥቷል፤ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንኑ አጽንቶታል፡፡

ይህን ተከትሎም አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት የአፈፃፀም ክስ ተጠሪ በዉሳኔዉ መሠረት እንዲፈጽምላቸዉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጎ አመልካች 12ኛ ክፍል ያጠናቀቁ በመሆናቸዉ ባላቸዉ የሙያ ችሎታ መሠረት ደመወዛቸዉን ብር 3400.00 በማድረግ በደረጃ 2 ላይ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

የመደባቸዉ መሆኑን እንዲሁም ክፍያም የተፈጸመላቸዉ መሆኑን ጠቅሶ ምላሽ ሰጥቷል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ይህንኑ መሠረት በማድረግ መርምሮ ፍርዱ ተፈጽሟል፤ ተጠሪ ያልከፈሏቸዉ ገንዘብ ካለ አመልካች መዝገቡን ማንቀሳቀስ ይችላሉ በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

አመልካች የስር ፍርድ ቤት በዚህ አግባብ በሰጠዉ ትዕዛዝ ባለመስማማት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን፣ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ የይግባኝ መዝገቡን አስቀርቦ የግራ ቀኝን ክርክር ከሰማ በኋላ በተጠሪ ድርጅት አዲስ መዋቅር የተሰራ መሆኑን፣ አዲስ በተሰራዉ መዋቅር መሠረት አመልካች ባላቸዉ የትምህርት ዝግጅትና የስራ ልምድ መሠረት ያደረገ ምደባ የሰጣቸዉ ስለመሆኑ ከቀረቡት የምደባ ደብዳቤ እና አዲሱ መዋቅር መሰራቱን ለማሳየት በማስረጃነት ከቀረበዉ ሰነድ መገንዘቡን፣ በዚህም መሠረት አመልካች ባላቸዉ የትምህርት ዝግጅት መሠረት በድርጅቱ ባለዉ ክፍት ቦታ ላይ ምደባ መስጠቱ የሚነቀፍ አይደለም በማለት በዚህ ረገድ የስር ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በማጽናት ዉዝፍ ደመወዝን አስመልክቶ የተሰጠዉን ዉሳኔ ግን በማሻሻል ወስኗል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም በዚሁ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካች ሰኔ 01 ቀን 2015 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚሉባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር ታርሞ እንዲወሰንላቸዉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የሰበር አቤቱታቸዉ መሠረታዊ ይዘትም በአጭሩ ተጠሪ በይግባኝ ደረጃ በተደረገዉ ክርክር የስራ መዋቅር ለዉጥ እንደተደረገና አመልካች በመዋቅሩ መሠረት ስሰራበት የነበረዉን የስራ መደብ የትምህርት ዝግጅት የማላሟላ መሆኑን በመግለጽ የተከራከረ ቢሆንም የስራ መዋቅር ነዉ የተባለዉ ሰነድ ደርሶኝ አስተያየት እንድሰጥበት አልተደረገም፡፡ አመልከች ከዉሳኔዉ በፊት ስሰራበት የነበረዉ መደቡ አሁን ደረጃ 6 ሆኗል፡፡ በስራ መደቡ ከ20 ዓመታት በላይ ስሰራ የቆየሁ በመሆኑ በአዲሱ ደረጃ 6 ሆኜ ደረጃዉ የሚፈቅደዉን ደመወዝ ማግኘት እችል ነበር፡፡ ሌሎች የድርጅቱ ሠራኞች ባሉበት የስራ መደብ ደረጃቸዉና ደመወዛቸዉ ብቻ ተስተካክሎ እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ ተጠሪ የለጠፈዉ ማስታወቂያም አልደረሰኝም፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ተሻሽሎ አመልካች ቀድሞ ወደነበሩበት የስራ መደብ እንዲመደቡ ይወሰንልኝ የሚል ነዉ፡፡

የሰበር አቤቱታዉ በችሎቱ ተመርምሮም ለአፈፃፀሙ መነሻ የሆነዉ ዉሳኔ ተጠሪ አመልካችን ወደ ስቶር ክለርክ የስራ መደብ እንዲመልስ የሚል ሆኖ ተጠሪ አመልካችን በድርጅቱ ባለዉ ሌላ ክፍት የስራ መደብ ላይ በሆነበት ሁኔታ እንደ ፍርዱ ተፈጽሟል በሚል የስር ፍርድ ቤቶች የደረሱበት ድምዳሜ ተገቢ መሆን አለመሆኑን ግራ ቀኝ በተገኙበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል ተብሏል፡፡ በዚህም መሠረት ተጠሪ ታህሳስ 30 ቀን 2016 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ከጥር 2014 ዓ.ም ጀምሮ ድርጅታዊ መዋቅር ከጸደቀ በኋላ ለምደባ እንዲያመች ተጨማሪ የትምህርት ዝግጅት ካላቸዉ እንዲያቀርቡ ተጠይቀዉ ማቅረብ ባለመቻላቸዉ በሚመጥናቸዉ ክፍት የስራ መደብ ላይ በቀድሞ ደመወዛቸዉ ላይ ጭማሪ በማድረግ ምደባ የሰጣቸዉ መሆኑን፣ ተጠሪ በዉሳኔዉ መሠረት ቀደም ሲል አመልካች ሲሰሩበት ወደነበረዉ ስራ የመመለስ ግዴታ ቢኖርበትም በመዋቅር ለዉጥ ምክንያት ክፍት የስራ መደብ ሳይኖር ሲቀር ግን ግዴታ የሌለበት መሆኑን ጠቅሶ ለጉዳዩ አግባብነት አላቸዉ የሚላቸዉን የተለያዩ የሰበር ዉሳኔዎችን በዋቢነት በመጥቀስ ጸንቶ እንዲወሰንለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡ አመልካች ጥር 16 ቀን 2016 ዓ.ም አዘጋጅተዉ ባቀረቡት የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸዉን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል፣ ይህ ችሎትም በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠዉ ዉሳኔ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም አመልካች ባቀረቡት የአፈፃፀም ክስ ለጠየቁት ዳኝነት መሠረት ያደረጉት ተጠሪ አመልካች ቀደም ሲል ሲሰሩበት በነበረዉ የስቶር ክለርክነት የስራ መደብ እንዲመለሱ የተሰጠዉን ዉሳኔ መሠረት በማድረግ ሲሆን፣ ተጠሪ በበኩሉ በዚህ መልኩ የተሰጠ ዉሳኔ መኖሩን ሳይክድ እንደ ዉሳኔዉ ተፈጽሟል በማለት የሚከራከረዉ ከዉሳኔዉ በኋላ በድርጅቱ በተደረገ የመዋቅር ለዉጥ መደረጉንና አመልካች የትምህርት ደረጃቸዉ 12ኛ ክፍል በመሆኑ አዲሱ የመዋቅር ለዉጥ የሚጠይቀዉን መስፈርት የማያሟሉ በመሆኑ በቀደመዉ የስራ መደብ ላይ መመደብ ባይችልም ደመወዛቸዉን ጨምሮ በሌላ የስራ መደብ ላይ የመደባቸዉ መሆኑን በመጥቀስ ነዉ፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ ፍርድ ቤት እንደ ፍርዱ ተፈጽሟል በሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰዉ አመልካች ባላቸዉ የሙያ ችሎታ ዉጤት የመረጃና ማህደር ባለሙያ 12ኛ ክፍል ያጠናቀቀ በመሆኑ አመልካችን በ3400 የደመወዝ መጠን በደረጃ 2 ላይ ተጠሪ የመደቧቸዉ መሆኑን በመጥቀስ ነዉ፡፡ በመሠረቱ አንድ ፍርድ እንደ ፍርዱ ተፈጽሟል ለማለት የሚቻለዉ በተወሰነዉ ዉሳኔ መሠረት የተፈጸመ ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 371 እና 378 ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም የአፈፃፀም አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤት እንደ ፍርዱ ተፈጽሟል ከሚል ድምዳሜ ላይ ከመድረሱ በፊት በርግጥም የፍርድ ባለ ዕዳዉ በፍርዱ በተመለከተዉ ሁኔታ የሚጠበቅበትን ግዴታ የተወጣ መሆን አለመሆኑን ለአፈፃፀሙ ምክንያት የሆነዉን ዉሳኔ ዓይነት እና ትክክለኛ ይዘት ባገናዘበ መልኩ በጥንቃቄ የመመርመር ኃላፊነት አለበት፡፡ ከዚህ አኳያ የተያዘዉ ጉዳይ ሲታይ በፍርዱ ላይ በተመለከተዉ ሁኔታ አመልካችን በስቶር ክለርክነት የስራ መደቡ ላይ አለመመደቡን፣ ይልቁንም በመዋቅር ጥናት ምክንያት አመልካችን በተጠቃሹ የስራ መደብ ላይ መመደብ የሚቻል ባለመሆኑ ሌላ ምደባ የሰጣቸዉ መሆኑን ጠቅሶ ተከራክሮ እያለ እና ይህም ተጠሪ በፍርዱ መሠረት አለመፈጸሙን የሚያሳይ ከመሆኑ አንፃር የስር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ በፍርዱ መሠረት ፈጽሟል ከሚል ድምዳሜ ላይ መድረሱ ስህተት በመሆኑ መታረም የሚገባዉ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡትን ቅሬታ ዉድቅ ያደረገዉ የተጠሪ ድርጅት አዲስ መዋቅር መስራቱንና በተሰራዉ አዲስ መዋቅር መሠረትም አመልካች ባላቸዉ የትምህርት ዝግጅትና የስራ ልምድ መሠረት ሌላ ቦታ የመደበ መሆኑ መረጋገጡን በመጥቀስ ነዉ፡፡ ፍርድ ቤቱ በዚህ የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ ሲደርስ መሠረት ያደረገዉም መዋቅሩ የተሰራበት ሰነድ እንዲሁም ለአመልካች የስራ ምደባ የተሰጠበትን ደብዳቤ አስቀርቦ በመመርመር ስለመሆኑ ከዉሳኔዉ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህም የሚያሳየዉ አመልካች ቀደም ሲል ሲሰሩበት የነበረዉ እና ለአፈፃፀም ምክንያት በሆነዉ ዉሳኔ ላይ የተመለከተዉ የስቶር ክለርክ የስራ መደብ አዲስ በተሰራዉ መዋቅር መሠረት የሚጠይቀዉን የትምህርት ደረጃ አመልካች የማያሟሉ በመሆኑ ተጠሪ በዉሳኔዉ መሠረት መመደብ አለመቻሉን ነዉ፡፡ በመርህ ደረጃ ፍርድ በፍርዱ በተመለከተዉ መሠረት ሊፈጸም የሚገባዉ ቢሆንም፣ በተለያዩ ምክንያቶች እንደ ፍርዱ ሳይፈጸም ሊቀር የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 392(2) ላይ ከተመለከተዉ ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለዉም እንደ ፍርዱ መፈጸም የማይቻልበት ሁኔታ ሲኖር አፈፃጸሙን የያዘዉ ፍርድ ቤት የአፈፃፀም ትዕዛዝ መስጠት የማይችል መሆኑን ነዉ፡፡ ከግል ስራ ክርክር ጋር በተያያዘ በፍርድ ቤት የተሰጠ ዉሳኔ አስቀድሞ በስራ ላይ

የነበረን ድርጅታዊ መዋቅርን መሠረት በማድረግ ሆኖ ጉዳዩ ለአፈፃፀም በቀረበ ጊዜ የድርጅቱ መዋቅር የተለወጠ መሆኑ ከተረጋገጠ ፍርዱ ሊፈጸም እንደማይችል የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 69471 (ቅጽ 13 ላይ የታተመዉ) ገዥ የህግ ትርጉም መገንዘብ ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ) ላይ በግልጽ እንደተመለከተዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉን ዉሳኔዎች በማረም ላይ የተገደበ ነዉ፡፡ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 በትርጉም ክፍል አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለዉ አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን፣ ህግ ያላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉን ህግ የሚጠቅስ፣ ለክርክሩ አግባብነት ያለዉ ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለዉ ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ ሲሆን፣ በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ዉድቅ በማድረግ ሲወሰን፣ በፍርድ አፈፃፀም ሂደት ከዋናዉ ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትዕዛዝ የተሰጠበት ሲሆን፣ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተሰጠ ዉሳኔ ሲሆን፣ የአስተዳደር አካል ወይም ተቋም ከህግ ዉጭ የሰጠዉ ዉሳኔ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ በመቃረን የተወሰነ ሲሆን ነዉ፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በሚል የሰበር አቤቱታ ሲቀርብለት ለአቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ ጉዳይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ ከላይ በዝርዝር ከተመለከቱት ሁኔታዎች ዉስጥ ቢያንስ አንዱን ያሟላ ሆኖ በዉጤቱም ጉልህ የሆነ የፍትሕ መጓደል የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ ከላይ ከተመለከተዉ የአዋጁ ድጋጌዎች ይዘት የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡

ከዚህ አንፃር የተያዘዉ ጉዳይ ሲታይ፣ አመልካች ቀደም ሲል ሲሰሩበት የነበረዉ እና ለአፈፃፀሙም መነሻ በሆነዉ ዉሳኔ ላይ የተመለከተዉ የስቶር ክለርክ የስራ መደብ በድርጅቱ በተሰራዉ የመዋቅር ለዉጥ ምክንያት አመልካች ካላቸዉ የትምህርት ደረጃ ከፍ ያለ የትምህርት ደረጃ የሚጠይቅ መሆኑ በፍሬ ነገር ረገድ መረጋገጡን ጠቅሶ የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ዉድቅ በማድረግ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በጸናዉ ዉሳኔ ላይ የተፈጸመ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>**ዉሳኔ**</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 302465 ላይ ሚያዝያ 04 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጡት ዉሳኔ በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1) መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ዉሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

የሰበር መ/ቁ/248492
ጥቅምት 04 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች፡ ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

ሡናይት አድነው

ሀፊዝ አባጀማል

አመልካቾች፤ 1. አቶ ሰለሞን ዱባለ -ቀረቡ

2. አቶ መስፍን ዮሀንስ -አልቀረቡም

ተጠሪዎች፤ 1. አቶ ተክለብርሃን ገ/ሚካኤል

2. ወ/ሮ እንከንየለሽ ገ/ሚካኤል

3. ወ/ሮ ጽጌ ገ/ሚካኤል

4. ወ/ሮ አሰገደች እሸቴ

(ተጠሪዎች 1–4) አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

**ፍርድ**

ጉዳዩ የዉል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ.300399 ግንቦት 17 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የፌዴራል የመጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት የሰጠው ትእዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት በሰበር ችሎት ታይቶ እንዲታረም የአሁን አመልካቾች ሰኔ 02 ቀን 2015 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡

ጉዳዩ በተጀመረበት የፌደራል መጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ከሳሽ አመልካቾች ተከሳሽ የነበሩ ሲሆን የተጠሪዎች ክስ ባጭሩ በግራ ቀኙ መካከል በ03/10/2013 ዓ.ም በተደረገ የቤት ሽያጭ ዉል በአራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 7 የቤት ቁጥር 036 የቦታው ስፋቱ 460 ካሬ የሆነ ቤት በብር 8,700,000.00 ለአመልካቾች የሸጡላቸዉና ቤቱን እና ቤቱን የሚመለከቱ ሰነዶችን ያስረከቧቸዉ መሆኑን ገልጸዉ ነገር ግን በተደረገዉ የቤት ሽያጭ ዉል ስምምነት ላይ ከሳሾች በሸጥንላቸዉ ቤት በስተምስራቅ በኩል ያለዉን ተለዋጭ መንገድ ለማስከፈት እና ተከሳሾች ደግሞ ብር 1,300,000.00 ሊከፍሉ ተስማምተን በዚሁ መሰረት ከሳሾች መንገዱን ያስከፈትን ሲሆን ተከሳሾች በገቡት ዉል ስምምነት መሰረት ገንዘቡን ሊከፍሉ ስላልቻሉ በውሉ የተመለከተውን ብር 1,300,000.00 እና ለክሱ ካወጣነዉ ወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፍሉን ይወሰንልን የሚል ነዉ፡፡

ተከሳሾች በሰጡት መልስ በግራ ቀኙ መካከል የቤት ሽያጭ ዉል መኖሩን አምነዉ ከሳሾች በዉሉ መሰረት በስተምስራቅ ያለዉን ተለዋጭ መንገድ በ2ወር ጊዜ ዉስጥ አስከፍተዉና የተከፈተዉን መንገድ የገረጋንቲ የድንጋይና የአሸዋ ሙሌት ስራ ሲፈጽሙ የተባለዉን ብር 1,300,000.00 ለሚሰራበት ሥራ ለመክፈል ተስማምተን እያለ ከሳሾች ከዉሉ ዉጭ መንግስት ከቤቱ ሽያጭ ዉል በፊት በንድፍ ወይም በእስኬች ያዘጋጀዉን የአየር ካርታ ማስረጃ ምንም ወጪ ሳያወጡበት ከመንግስት ያገኙት ማንኛዉም ሰዉ ባለመብትነቱን በማረጋገጥ የግል ይዞታ ላለዉ የሚሰጥ መረጃ እንጂ እንደ ካርታ የማያገለግል በቀን 06/08/2014 ዓ.ም ፕሪንት የተደረገ ሰነድ በማቅረብ ብቻ ያልሰሩበትን አገልግሎት መጠየቃቸዉ ያለአግባብ ለመበልጸግ የመሰረቱብን ክስ በመሆኑ ክሱ ዉድቅ ተደርጎ ወጪና ኪሳራ እንዲከፍሉ ይወሰንልን ሲሉ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የስር የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመመርመር ከሳሾች በዉሉ የተስማሙት መንገዱን በመሬት ላይ ለማስከፈት ሳይሆን በእስኬች ለማስከፈት ስለመሆኑ ባቀረቡት ማስረጃዎች የተረጋገጠ በመሆኑ እና የተጠቀሰዉ መንገድ በእስኬች መከፈቱም በተከሳሾች ያልተካድ በመሆኑ ተከሳሾች በዉላቸዉ መሰረት ብር 1,300,000.00 ለከሳሾች ሊከፍሉ ይገባል በማለት ለከሳሾች ወጪ ኪሳራ ዝርዝር የማቅረብ መብታቸዉን ጠብቆ ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካቾች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታ ያቀረቡ ሲሆን ከፍተኛ ፍርድ ቤቱም የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ዉሳኔ በማጽናት የአመልካችን የይግባኝ ቅሬታ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም ይህንን የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ይዘት በአጭሩ፤ የስር ፍርድ ቤቶች ውሉ ሊፈጸም የማይችል መሆኑን ገልጸን ያቀረብነዉን መቃወምያ ብይን ሳይሰጥበት ታልፎ ውሳኔ መስጠቱ፤ ውሉ እንደ ስምምነቱ ባልተፈጸመበትና የተባለው መንገድ በእስኬች ይከፈታል የሚል ስምምነት ባልተደረገበት ሁኔታ መንገዱ በእስኬቹ የተከፈተ ነው በማለት አመልካቾች ውሉ ላይ የተጠቀሰውን ገንዘብ አመልካቾች እንድንከፍል ዉሳኔ መሰጠቱ ተገቢ ያልሆነ እና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነዉ፡፡

የአመልካችም አቤቱታ በሰበር ችሎት ተመርምሮ አንድ ተዋዋይ ወገን እንደ ዉሉ እንዲፈጸምለት መጠየቅ የሚችለዉ ከዉሉ ስምምነት የተነሳ የበኩሉን ግዴታ ሲወጣ ስለመሆኑ በፍ/ሕ/ቁ.1757 እና ተከታይ ድንጋጌዎች የተመለከተ እንዲሁም የዉል አፈጻፀም መሰረታዊ መርህ ከመሆኑ አንጻር የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ብር 1,300,000.00 አመልካቾች እንዲከፍሉ የሰጠዉ ዉሳኔ ተጠሪዎች በበኩላቸው በዉሉ የተመለከተዉን መንገድ የማስከፈት ግዴታ በአግባቡ መወጣታቸው ተረጋግጦ መሆን አለመሆኑን አጣርቶ ለመወሰን ሲባል መዝገቡ ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ታዟል፡፡

ተጠሪዎች ህዳር 11 ቀን 2016 ዓ/ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል ይዘቱም፤ የሥር ፍርድ ቤቶች በግራቀኛችን መካከል የተደረገው ውል በመካከላችን ሕግ እንደሆነ የፍ/ሕ/ቁ 1731 እና የፍ/ሕ/ቁ 1733 ድንጋጌን በመጥቀስ ውለታዎች ግልጽ በሆነ ጊዜ የተዋዋዮች ፍቃድ ምን እንደሆነ ለመተርጐም የማይቻል እና በውሉ ላይ በግልጽ የተጠቀሰውን ብቻ መከተል እንደሚገባ አጽንኦት በመስጠት ውሉን በመመልከት እና በውሉ ላይ የፈረሙ ምስክሮችን ቃል በመስማት ተጠሪዎች በውል የተመለከተውን መንገድ የማስከፈት ግዴታ የተወጣን መሆኑን ከቀረበው ሰነድና የሰው ምስክር ጭምር በማረጋገጥ እና በማጣራት የሰጡት ውሳኔ በመሆኑ የሚነቀፍ እና መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም ስለሆነም ሊጸና ይገባል ያሉ ሲሆን አመልካቾችም አቤቱታቸዉን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

የጉዳዩ አመጣጥና የክርክሩ ይዘት በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን ይህ ችሎትም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን ያለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አኳያ እና ከተገቢው ህግ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደ መረመርነዉም በግራ ቀኙ መካከል ተጠሪዎች ለአመልካቾች ከሸጡት ቤት በስተቀኝ ያለውን ይዞታ ተጠሪዎች ለማስለቀቅ አመልካቾች ደግሞ ብር 1.300,000.00 ሊከፍሉ ይህ ስምምነት ሲጠናቀቅ ለአመልካቾች ስም ሊዞርላቸው የተዋዋሉ መሆኑ አከራካሪ አይደለም ከግራ ቀኙም ውል መገንዘብ የተቻለ ጉዳይ ነው ግራ ቀኙን ያከራከረው ጉዳይ አመልካቾች በውሉ መሰረት ተጠሪዎች የተባለውን ቦታ አላስለቀቁልንም የሚል እና በዚህም ምክንያት የተባለውን ገንዘብ ለመክፈል አንገደድም የሚል ሲሆን የተጠሪዎች ክርክር የተባለውን ቦታ በውሉ መሰረት በስኬች አስለቅቀን አስረክበናል በመሆኑም በውሉ መሰረት ግዴታችንን የተወጣን ስለሆነ የውሉን ገንዘብ ሊከፍሉን ይገባል የሚል ነው፡፡

የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ፣ የተባለውን ውል አስቀርቦ በማየት እና በውሉ ላይ የነበሩ ምስክሮችን አስቀርቦ በመስማት የበለጠ የተረጋገጠው ተጠሪዎች በውሉ መሰረት አከራካሪውን ይዞታ በማስለቀቅ እና ለአመልካቾች በማስረከብ ግዴታቸውን የተወጡ መሆኑን ደምድሞ አመልካቾች በውሉ የተመለከተውን ገንዘብ ብር 1,300,000.00 ለተጠሪዎች ሊከፍሉ ይገባል በማለት በሰጠው ውሳኔ የአሁን አመልካቾች ቅር ተሰኝተው ለፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታቸውን ቢያቀርቡም የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካቾች ያቀረቡትን የይግባኝ ቅሬታ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 337ን በመጥቀስ ውድቅ በማድረግ ትእዛዝ መስጠቱን እና በግራ ቀኙ መካከል ግንቦት 14 ቀን 2014ዓ.ም ተደረገ የተባለው ውል ተጠሪዎች በውሉ መሰረት የተባለውን ቦታ ለአመልካቾች ሲያስለቅቁላቸው በቤቱ ሽያጭ ውል መሰረት ተጠሪዎች ለአመልካቾች ስም ለማዞር የተዋዋሉ መሆናቸውን ቢገልጽም አመልካቾች በውሉ መሰረት ተጠሪዎች የተባለውን መንገድ ባለማስለቀቃቸው ስም አልዞረልንም በማለት ያነሱት መከራከሪያ የሌለ መሆኑን ከሰር ፍርድ ቤቶች የውሳኔ ግልባጮች መረዳት ችለናል፡፡

በመሆኑም አመልካቾች በውሉ መሰረት ተጠሪዎች ግዴታቸውን ያልተወጡ ስለሆነ በውሉ የተመለከተውን ገንዘብ ክፈሉ ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም ሊሻር ይገባል በማለት ያቀረቡትን ቅሬታ ከሰበር ሰሚው ችሎት ስልጣን አንጻር ስንመረምረው በኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ ላይ እንደተደነገገው የሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን የመጨረሻ ዉሳኔ በተሰጠባቸዉ ጉዳዮች ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞ ሲገኝ ይህንኑ በማረም ላይ የተገደበ

ከመሆኑም በተጨማሪ በሰበር ሊታረም የሚገባ መሰረታዊ የህግ ስህተት የሚያሰኙት ምክንያቶች በፌደራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2/4/ እና 10 ተዘርዝረው የሚገኙት ናቸው የእነዚህ የህግ ድንጋጌዎች ይዘት ሰበር ሰሚ ችሎት የተቋቋመበትን ዓላማ ማለትም ወጥ የህግ አተረጓጎም እንዲኖር እና የዉሳኔዎችን ተገማችነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በመስጠት እንዲሰራ ከተዘረጋው ከሰበር ስርዓት መሰረታዊ ዓላማም የምንገነዘበዉ ጉዳይ ነዉ፡፡

በተጨማሪም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅጽ 9 በመዝገብ ቁጥር 41526 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ከዚህ ሁሉ አንጻር ስናየው ሰበር ሰሚ ችሎቱ የፍሬ ነገር ክርክር የማጣራት፣ ማስረጃ የመመርመር እና የመመዘን ስልጣን በህግ ያልተሰጠው መሆኑን ነዉ፡፡ ስለሆነም አመልካቾች በዚህ ረገድ ያቀረቡት ቅሬታ የፍሬ ነገር እና የማስረጃ ምዘና ላይ ያተኮረ በመሆኑ በዚህ ችሎት ሊመረመር እና ሊታይ የሚገባው ሆኖ አላገኘነውም፡ በመሆኑም ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ዉሳኔ

1.የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.300399 ግንቦት 17 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት በዋለዉ ችሎት የፌዴራል የመጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠዉን ውሳኔ በማጽናት የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡

2.በዚህ ፍርድ ቤት ለተደረገዉ ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡
3.በዚህ ጉዳይ አስቀድሞ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁ 238057 ተጀምሮ የነበረውን አፈጻጸም በማገድ የተሰጠ ትእዛዝ ተነስቷል ይጻፍ፡

4.የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት


የሰበር መ/ቁ. 248670
ጥቅምት 05 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች፡ ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

ሠናይት አድነው

ሀፊዝ አባጀማል

አመልካች፦ ወ/ሮ ፈቲያ አህመድ ጀማል

ተጠሪዎች፦ 1. ወ/ሮ ዘሀራ በድሩ

2. አቶ ጀማል አባስ

3. ወ/ሮ ዚያዳ ሽኩር

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

## ፍርድ

ጉዳዩ የሽያጭ ዉልን የሚመለከት ሲሆን ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው በደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ/ የስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 16775 ነሐሴ 13 ቀን 2014 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ፤ የደብ/ብ/ብ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.20663 ታህሳስ14 ቀን 2015


ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.22079 መጋቢት 06 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት በሰጠዉ ተዕዛዝ ላይ ተፈጽሟል ያሉትን መሠረታዊ የሕግ ስህተት በመጥቀስ በሰበር ታይቶ እንዲታረም የአሁን አመልካች ሰኔ 05 ቀን 2015 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡

ጉዳዩ በተጀመረበት የስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት 1ኛ ተጠሪ ከሳሽ፣ አመልካች እንዲሁም 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች እንደየቅደም ተከተላቸዉ 1ኛ፣ 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች የነበሩ ሲሆን የተጠሪ ክስ ባጭሩ፤1ኛ ተጠሪ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በ1987 ዓ.ም ጋብቻ ፈጽመዉ 5 ልጆች እና ንብረት ያፈሩ መሆኑን እና በመካከላቸዉ በተፈጠረዉ ያለመግባባት ጋብቻዉ በ2005 ዓ.ም የፈረሰ በመሆኑ በጋብቻ ላይ ሳሉ በወራቤ ከተማ ቀበሌ 02 500ካ.ሜ ላይ ያረፈ እና ስመ ሀብቱ በ2ኛ ተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኘዉን ቤት ድርሻዬን እንዲያካፍለኝ ክስ አቅርቤ እና 3ኛ ተከሳሽም ሚስት ነኝ ድርሻ አለኝ በማለት የጣልቃ ገብ ክርክር አቅርበው ፍርድ ቤቱ አከራክሪውን ቤት ለ3 እንድንካፈል ውሳኔ ሰጥቶ ባለበት ሁኔታ 1ኛ ተከሳሽ ይህንን ቤት ከ2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች የገዛሁት ቤት ስለሆነ የተሰጠው ውሳኔ መብቴን ይነካል ይሻርልኝ የሚል ክርክር አቅርበው መልስ እንድሰጥ ስታዘዝ ይህ መሆኑን አውቄያለሁ ሆኖም 1ኛ ተከሳሽ ቤቱን ገዛሁ የሚሉት ሚያዝያ 23 ቀን 2003ዓ.ም ሲሆን አስቀድሞ በነበረው ክርክር 2008ዓ.ም ላይ 2ኛ ተከሳሽ ቤቱን በእዳ አስይዤዋለሁ ከማለት በስተቀር እና 3ኛ ተከሳሽም ድርሻዬ ይወሰንልኝ ከማለት በስተቀር 2003ዓ.ም ቤቱ የተሸጠ መሆኑ አንስተው ያቀረቡት መከራከሪያ የሌለ በመሆኑ ቤቱን አስቀድመው ያልሸጡት እና ሆን ብለው ቀኑን ወደ ኋላ ወሰድው ያደረጉት ሀሰተኛ ውል ከመሆኑም በተጨማሪ ውሉ የመንደር ውል በመሆኑ ረቂቅ እና በህግ አግባብ ያልተመዘገበ በመሆኑ የኔ እና የ2ኛ ተከሳሽ ጋብቻ ከመፍረሱ በስተቀር ንብረት ክፍፍል ያልተደረገበት ንብረት በመሆኑ ለመሸጥ የኔ ፍቃድ የሚስፈልግ ስለሆነ እና የእኔ ፍቃድ የሌለበት ውል በመሆኑ ሆን ተብሎ በተንኮል ተግባር የተፈጸመ ውል መሆኑ ተረጋግጦ የሽያጭ ዉል የለም እንዲባልልኝ አለም ከተባለ በህገ ወጥ መንገድ የተፈጸመ በመሆኑ ፈራሽ ነዉ ተብሎ እንዲወሰንልኝ እና ተከሳሾች ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ እና በዚህ ክስ ምክንያት የደረሰብኝን ወጪ እና ኪሳራ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ የሚል ነዉ፡፡

አመልካች የሆኑት የስር 1ኛ ተከሳሽ በሰጡት መልስ 2ኛ ተጠሪ ከ1ኛ ተጠሪ መስከረም 26 ቀን 1997 ዓ.ም በተጻፈ በተሰጣቸው ሙሉ ዉክልና መሰረት የጋራቸዉ የሆነዉን ይህን ቤት ሚያዝያ 23 ቀን 2003 ዓ.ም በተደረገ የቤት ሽያጭ ዉል ቤቱን ሽጠውልኝ ቤቱንም ከ10ዓመት በላይ የተገለገልኩበትና የተለያዩ ማሻሻያዎች ያደረኩበት በመሆኑ እና በዉክልናዉ መሰረት የተደረገ የሽያጭ ዉል በመሆኑ ሊፈርስ ስለማይገባ ክሱ ዉድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾችም በነበረብን እዳ ምክንያት 1ኛ ተጠሪ ዉክልና ለ2ኛ ተጠሪ ሰጥታኝ ቤቱ በ400,000 ብር እንዲሸጥ አድርገዋል ለረጅም ጊዜ ዉል ይፍረስልኝ ጥያቄ አላቀረቡም ቤቱን ሸጠን እዳዉም ተከፍሏል በመሆኑም አሁን ዉል ይፍረስልኝ በማለት የቀረበዉ ክስ ያላግባብ ስለሆነ ዉሉ ጸንቷል ተብሎ ክሱ ዉድቅ ይደረግልን በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤትም የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመመርመር 1ኛ ተጠሪ ለ2ኛ ተጠሪ ዉክልና መስጠታቸው የታመነ ቢሆንም 2ኛ ተጠሪ ሽያጩን ያከናወኑት 1ኛ ተጠሪን ሳያካተት 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪ ሻጭ ሆነዉ የተፈጸመ የሽያጭ ዉል ነዉ ይህ ደግሞ 2ኛ ተጠሪ ዉሉን በራሳቸው ስም የፈጸሙት የሽያጭ ዉል በመሆኑ እና 1ኛ ተጠሪ ፈቃድ ያልሰጡበት በመሆኑ የሽያጭ ዉሉ ሊፈርስ ይገባል፡፡ በተጨማሪም የአሁን አመልካች በስር ክርክር መልሳቸው የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በማቅረብ በቤቱ ላይ ማሻሻያ አድርገው ከሆነ ዉሉ ቢፈርስ በማለት በአማራጭ ያቀረቡት ክርክርም የለም በማለት የሽያጭ ዉሉ መፍረስ ውጤትን በተመለከተ በዝምታ በማለፍ ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም በመ/ቁ.20663 ታህሳስ 14 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ዉሳኔ በማጽናት የወሰነ ሲሆን የክልሉ ሰበር ችሎቱ ደግሞ ጉዳዩ የፌደራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን ስር የሚወድቅ በመሆኑ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት በመ/ቁ.22079 መጋቢት 06 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት ተዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም ይህን የስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘት በአጭሩ የአሁን ተጠሪዎች ባልና ሚስት በመሆናቸው በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 25890 ለነበራቸው ክርክር የሰጡትን መልስ ለአሁን ክርክር መሰረት ተደርጎ የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ የፌ/ሰበር ችሎት የ/ሰ/መ/ቁ 80723 ቅጽ 14 በመጥቀስ በሌላ መዝገብ ላይ የተሰጠ ምስክርነት ቃል በክርክሩ ባልተሳተፈ ሰዉ ላይ ተፈጻሚ አይሆንም በማለት የሰጠውን ውሳኔ የሚጻረር በመሆኑ ተገቢነት የለውም፣ ወኪል የሆነው ሰው ውክልናውን በሚገባ እስካሳየ ድረስ የራሱን ወይም የወካዩን ስም መጻፉ ወኪልነቱን የማያስቀር መሆኑን የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በቅጽ 5 በሰ/መ/ቁ 23861 እና እንደራሴው ከወኪልነቱ ስልጣን ሳያልፍ የፈጸማቸው ተግባሮች በቀጥታ በሿሚው እንደተፈጸመ የሚቆጠር ስለመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ 2189(1) ላይ የተመለከተ በመሆኑ የሽያጭ ውሉ የተፈጸመዉ የ1ኛ ተጠሪን ጥቅም ለመጉዳት በማሰብ መሆኑን አመልካች የሚያውቅ ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ በሌለበት ዉሉ ይፍረስ መባሉ አግባብ አይደለም፣ ውል እንዲፈርስ ሲወሰን ተዋዋይ ወገኖች ወደነበሩበት ይመለሱ በማለት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ውሳኔ መስጠት የሚቻለው መመላለሱ አንደኛውን ወገን በእጅጉ የሚጎዳ ለሌላኛው ወገን ያልተገባ ጥቅም ሊያስገኝ የሚችል አለመሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ስለመሆኑ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅጽ 8 በሠ/መ/ቁ 39336 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠ ሲሆን የውል መፍረስ ውጤትን ተከትሎ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1815(1) መሰረት ተዋዋይ ወገኖች ወደነበሩበት እንዲመለሱ መወሰን እየተገባ የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት ግን የአሁን አመልካች ውሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት ከመከራከር ባለፈ ውሉ ቢፈርስ በአማራጭ መከራከሪያ አላቀረበችም በሚል ምክንያት ተዋዋይ ወገኖች ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ እንኳን ያለመወሰኑና ይኸዉም ዉሳኔ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም መጽናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነዉ፡፡

የአመልካችም አቤቱታ በሰበር ሰሚዉ ችሎት ተመርምሮ በአመልካችና በ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች መካከል የተፈጸመዉ የቤት ሽያጭ ዉል እንዲፈርስ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ የሰጠ ቢሆንም አመልካች የከፈሉትን በተመለከተ ምንም ሳይል ማለፉን ከፍ/ህ/ቁ.1815/1/ እንዲሁም በቤቱ ላይ የተደረገዉ መሻሻል አስመልክቶ የሰጠዉን ዉሳኔ ለመመርመር ሲባል ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ታዟል፡፡

1ኛ ተጠሪ ህዳር 13 ቀን 2015 ዓ/ም የተፃፈ መልስ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፤ ወደ ነበሩበት ይመለሱ ተብሎ ሊወሰን የሚገባው 1ኛ ተጠሪ የውሉ አካል ብሆን ነበር 1ኛ ተጠሪ በአመልካችና በሌሎች ተጠሪዎች መካከል በተደረገ ውል እኔ 3ኛ ወገን በመሆኔ እና የሌለሁበት ውል እንዲፈርስ በጠየቅኩት መሰረት ፍርድ ቤቱ መወሰኑ ተገቢ ሲሆን ውሉ ይፍረስ መባሉ ውል ስለመኖሩ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ስላልካዱ ወደ ነበሩበት የማይመለሱበት ምክንያት የለም፣ ይህም አመልካች 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችን በሌላ መዝገብ ከሰው የሚጠይቁ ከመሆኑ ውጪ ውሉ ይፍረስ መባሉ ወደ ነበሩበት ይመለሱ ቢባልም ባይባልም በውጤት ረገድ የተለየ ነገር የሌለው በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል አያስብልም፡፡ ቤቱ ላይ የተደረገ ማሻሻያን አስመልክቶ አመልካች በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 182(2) መሰረት በግልፅ ዳኝነት ጠይቀው ባልተከራከሩበት ፍርድ ሊሰጥ ስለማይቻል ፍርድ ይሰጥ ቢባል እንኳን አመልካች መሻሻልን አስመልክቶ ቤቱን ከገዛሁት በኋላ አሻሽዬዋለሁ ከማለት ውጭ ማስረጃ በማቅረብ አላስረዱም በዋናነት ማሻሻያ ተደርጓል አልተደረገም የሚለው የማስረጃ ምዘና ጉዳይ ሲሆን ሰበር ሰሚ ችሎቱ ማስረጃን የመመዘን ሥልጣን በህጉ ያልተሰጠው በመሆኑ በዚህ ደረጃ ሊቀርብ የማይችል በመሆኑ፤ በስር ፍርድ ቤቶች ማስረጃ ምዘናን አስመልክቶ የተፈፀመ የህግ ስህተት የሌለ ስለሆነ  በአጠቃላይ የስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ የሚነቀፍ እና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስላልሆነ ሊጸና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችም የካቲት 21 ቀን 2016 ዓ.ም በተጻፈ መልስ ከ1ኛ ተጠሪ በ1997 ዓ.ም ሰኔ ለ2ኛ ተጠሪ በተሰጠኝ ህጋዊ ዉክልና መሰረት ስለ እራሴና ስለ 1ኛ ተጠሪ ፈርሜ እንዲሁም ከ3ኛ ተጠሪ ጋር በመሆን በጋራ ተስማምተን ቤቱን በ400,000 ብር ለአመልካች የሸጥን በመሆኑ ቤቱ የአመልካች ነዉ ተብሎ እንዲወሰን እንጠይቃለን ብለዋል፡፡ አመልካችም አቤቱታቸዉን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና የክርክሩ ይዘት በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን ይህ ችሎትም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አኳያ እና ከተገቢው ህግ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነዉም በአመልካችና 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች መካከል ሚያዝያ 23 ቀን 2003 ዓ.ም ተደረገ የተባለው የቤት ሽያጭ ዉል ሊፈርስ አይገባም በማለት በአመልካች የቀረበውን መከራከሪያ በተመለከተ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት አከራካሪው ቤት የተጠሪዎች የጋራ ሀብት መሆኑን፣ በዚህም ምክንያት ለ3 እንዲካፈሉ የተሰጠ የፍርድ ውሳኔ መኖሩን፣ ይሁን እንጂ ቤቱ ክፍፍል ያልተደረገበት እና 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ለአሁን አመልካች ሲሸጡ የአሁን 1ኛ ተጠሪ የሆኑት የጋር ባለሃብት ፍቃዳቸውን ያልሰጡ መሆኑ የተረጋገጠ መሆኑን በመግለጽ በአመልካች እና በ2ኛ እና በ3ኛ ተጠሪዎች መካከል ተደረገ የተባለው ውል የፍቃድ ጉድለት ያለበት ነው በማለት አትቶ የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1808(1)ን በመጥቀስ ውሉ ሊፈርስ ይገባል በማለት ውሳኔ የሰጠ እና ይህ ውሳኔ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን ከስር ፍርድ ቤቶች የውሳኔ ግልባጮች መረዳት የቻልን ከመሆኑም በተጨማሪ የአሁን 1ኛ ተጠሪ ውሉ እንዲፈርስ ባቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ላይ ውሉ የህጉን መስፈርት ያላሟላ ስለሆነ ረቂቅ ነው በመሆኑም ሊፈርስ ይገባል በማለት ላነሱት መከራከሪያ አመልካች ውሉ ከረቂቅነት ያለፈ እና ሊፈጸም የሚችል ውል መሆኑን አንስተው ያቀረቡት ክርክር እና ማስረጃ የሌለ ስለሆነ በዚህ አግባብም ውሉ በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1808(2) መሰረት ከተዋዋዩቹ አንዱ ወይም ማንኛውም ጥቅም ያለው ሰው ውሉ እንዲሠረዝ በሚያቀርበው ጥያቄ ሊፈርስ የማይችልበት አግባብ ስለሌለ አመልካች ውሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት ያቀረቡት መከራከሪያ ተቀባይነት ያለው አይደለም አጣሪው ችሎትም ጭብጥ አድርጎ አልያዘውም፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚመጣው ጉዳይ የውል መፍረስ ውጤት ምንድነው? የሚለው ነው በመሰረቱ በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1815(1) ላይ እንደተመለከተው የውሉ መፍረስ ውጤቱ በተቻለ መጠን ተዋዋዩቹ ውለታ ከመደረጉ በፊት ወደነበሩበት ሁኔታ እንዲመለሱ ማድረግ መሆኑን ደንግጎ

ወደነበሩበት እንዲመለሱ ሲወሰን ውለታውን ለመፈፀም የተሠራ ሥራ ሁሉ ቀሪ እና ውጤት የሌለው እንደሚሆን የተጠቀሰው አንቀፅ ንዑስ ቁጥር 2 ይገልፃል፡፡ ይኸው የፍትሐብሔር ሕጉ አንቀፅ 1817(1) እና (2) ውለታውን ለመፈፀም የተሰራውን ሥራ ለማፍረስ የማይቻል ሲሆን ወይም አስቸጋሪ ሆኖ ሲገኝ ወይም ከፍ ያለ መሰናክል የሚያመጣ ሲሆን እነዚህ የተሰሩት ሥራዎች እንደረጉ እንዲቀሩ ይደረጋል በማለት ይደነግጋል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሉ እንዲፈርስ ከወሰነ በኋላ በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1815(1) መሰረት ተዋዋዮቹ ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ ያልወሰነው አመልካች ውሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት በስር ፍርድ ቤት ክርክራቸውን ሲያቀርቡ በአማራጭ ውሉ የሚፈርስ ከሆነ ወደነበርንበት እንድንመለስ ይወሰንልኝ በማለት ያቀረቡት መከራከሪያ የለም በማለት ነው፡፡

በመሰረቱ በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1815(1) ላይ እንደተመለከተው የውል መሰረዝ ወይም መፍረስ ውጤቱ ተዋዋዮችን በተቻለ መጠን ወደ ነበሩበት መመለስ መሆኑን ደንግጎ ይገኛል፡፡ ይህ ማለት ህጉ ለውል መሰረዝ ወይም መፍረስ ያስቀመጠው መፍትሄ እንጂ በተዋዋይ ወገኖች ጥያቄ ላይ ብቻ ተመስርቶ ዳኝነት ሊሰጥበት የሚገባ ጉዳይ እንዳልሆነ ከድንጋጌው ይዘት መረዳት የሚቻል ጉዳይ ነው፡፡

ስለሆነም አንድ ፍርድ ቤት በቀረበለት ጉዳይ ላይ ውል እንዲፈርስ የሚወስን ከሆነ ተዋዋዮች ከውለታቸው በፊት ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ መወሰን የፍርድ ቤት ሃላፊነት እንጂ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 182(2) ላይ በተደነገገው አግባብ የተከራከሪ ወገኖች የክርክር አቀራረብ ጉዳይ አይደለም፡፡ በመሆኑም የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሉ እንዲፈርስ ከወሰነ በኋላ የተከራካሪዎቹን የክርክር ይዘት ከግምት ሳያስገባ በፍ/ብ/ህግ.ቁጥር 1815(1)፣1817(1) እና (2) መሰረት ተዋዋዮቹ ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ መወሰን ሲገባው አመልካች በስር ክርክራቸው አላቀረቡትም በማለት ሳይወሰን ማለፉ እና ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ይህንን ስህተት ሳያርም የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>**ዉሳኔ**</u>

<u>ማስታወሻ</u>፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

1.የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 20663 በ14/4/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስልጢ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካች እና በ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች መካከል የተደረገው ውል እንዲፈርስ የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡

2.ከውሉ መፍረስ ውጤት ጋር ተያይዞ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካች የቀረበ አማራጭ ክርክር የለም በማለት አትቶ ሳይወስን በማለፍ የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከላይ በተጠቀሰው መዝገብ ቁጥር እና ቀን የሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

3.የስልጢ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ የውሉ መፍረስ በተዋዋዮቹ መካከል የሚያስከትለውን ውጤት በተመለከተ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃዎች ከፍ/ት/ብ/ህግ ቁጥር 1815(1)፣ 1817(1) እና (2) አንጻር አጣርቶ የመሰለውን እንዲወስን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሠረት ይመለስ ብለናል፡፡

4.በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

5.የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ተመላሽ ይደረግ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ.248862

ጥቅምት 04 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች፡-ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

ሠናይት አድነው

ሀፊዝ አባጀማል

አመልካች ፡- አቶ ተወልደ አፈወርቅ

ተጠሪዎች ፡-1. አቶ ወንድማገኝ ቢያሳልፍ

2. አቶ ፍቃዱ ቢያሳልፍ

3. አቶ ደረጄ ቢያሳልፍ

4. አቶ ታሪኩ ቢያሳልፍ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የቤት ሽያጭ ውልን የሚመለከት ክርክር ሲሆን ክርክሩ በፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲጀመር የአሁን አመልካች ከሳሽ ሲሆኑ የአሁን ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሾች ናቸው፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አመልካች በፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት ክስ የተጠሪዎች አውራሽ ከሆኑት የተጠሪዎች እናት ወ/ሮ አስራቴ ቤዛ እና የተጠሪዎች አባት አቶ ቢያሳልፍ መንገስቱ ጋር ህዳር 06 ቀን 2008 ዓ.ም በፈፀምነው የቤት ሽያጭ ውል በካድስተር ቁጥር 412122800900 በተጠሪዎች አባት ስም ተመዝግቦ ከሚገኘው ይዞታቸው ላይ በመቀነስ በ154 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ያረፈውን ቤት በብር 610,000.00 ሊሸጡልኝ ተስማምተን ብር 400,00.00 በመክፈል ቤቱን ተረክቤ በማከራየት የአከራይ ተከራይ ግብር እየከፈልኩ የምገኝ ሲሆን፤ የተጠሪዎች አውራሾች የሊዝ ክፍያን ከፍለውና በተጠሪዎች አባት ስም ካርታ አውጥተው በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ ጽ/ቤት ቀርበው ስመ ሀብቱን ሊያዞዋውሩልኝ ተስማምተን የነበረ ቢሆንም በስምምነታችን መሰረት የተጠሪዎች አባት ሳይፈፅሙ የሞቱ ሲሆን የተጠሪዎች እናትም በስምምነታችን መሰረት ለመፈፀም ፍቃደኛ አልነበሩም፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች ከአውራሾቻቸው ጋር በፈፀምኩት ውል መሰረት እንዲፈፅሙልኝ በውሉ መሰረት መቀጮ፣ ወጪና ኪሳራ እንዲከፍሉኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪዎች በሰጡት መልስ አውራሾቻችን ስለ ሽያጭ ውሉም ሆነ ክፍያ ስለመቀበላቸው አልነገሩንም እኛም አላየንም፣ አመልካች ወላጆቻችን በህይወት እያሉ መጠየቅ ይችሉ ነበር አልጠየቁም ማስጠንቀቂያ ያልሰጡንና ውርሱ ሲጣራም ያልተቃወሙ በመሆናቸው እና አመልካች ያቀረቡት ውል ወላጆቻችን ያልፈረሙት በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1723 ላይ የተቀመጠውን የህግ መስፈረት ያላሟላ በሕግ አግባብ ያልተደረገ የመንደር ረቂቅ ውል ስለሆነ ሊያስገድደንም ሆነ መቀጮ ሊያስቀጣን አይችልም፡፡ አውራሾቻችን አመልካች ለሚጠቀሙበት ቦታ የሊዝ ግብር የሚከፍሉበት አግባብ ካለመኖሩም በላይ የድርጅት ሽያጭ ሆኖ ሳለ በስህተት የቤት ሽያጭ የተባለ በመሆኑ አመልካች ያቀረቡት ክስ ውድቅ እንዲደረግና ወጪና ኪሳራችንን እንዲተኩልን ብለዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር እና ምስክሮች ሰምቶ አመልካች እና የተጠሪዎች አውራሽ የፈፀሙት የመንደር የቤት ሽያጭ ውል ነው፤በሰ/መ/ቁ.21448 እና የፍ/ብ/ሕ/ቁ.2723(1) እና 2878 መሰረት አመልካችና የተጠሪዎች አውራሽ የፈፀሙት የቤት ሽያጭ ውል በሚመለከተው አካል ፊት ያልተደረገና ያልተመዘገበ የመንደር ወል ስለሆነ እንደረቂቅ የሚቆጠርና በሕግ ፊት የማይፀና ውል ነው በማለት ደምድሞ የአመልካችን ክስ ውድቅ በማድረግ አመልካች በውሉ መነሻነት የፈፀሙት ክፍያ ካለ አዲስ ክስ አቅርበው የመጠየቅ መብታቸው ተጠብቋል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አመልካችም በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ ያቀረቡ ቢሆንም ይግባኝ ሰሚው ችሎት ቅሬታውን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.337 መሰረት ውድቅ በማድረግ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካችም ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ሰኔ 09 ቀን 2015 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ የሰበር አቤቱታቸውም ከተጠሪዎች አውራሾች ጋር የሰነድ አልባ ቤት የሽያጭ ውሉ መፈፀሜና ቤቱን ተረክቤ እያስተዳደርኩ የምገኝ መሆኑ በመረጋገጡ ውሉ በተዋዋዮች መካከል የሚፀና ሆኖ ሳለና ተጠሪዎችም ሟች ወላጆቻቸውን የሚተኩ እንጂ 3ኛ ወገን ባለመሆናቸው፣ ውሉንም መካድ እንደማይችሉ እየታወቀ ውሉ ባለመመዝገቡ ብቻ ተፈፃሚነት የለውም መባሉ አግባብ አይደለም፡፡ ተጠሪዎች የቤት ሽያጭ ውሉን በግልጽ ክደው ሳይከራከሩ ፍ/ቤቱ በራሱ ተነሳሽነት ውሉ ረቂቅ ውል ነው በማለት ዳኝነት ሳንጠይቅ ክፍያውን በሌላ መዝገብ ጠይቁ ብሎ ውሳኔ ማሳለፉ አግባብነት የለውም፡፡ በሥር ፍ/ቤት ተጠሪዎች መልስ የመስጠት መብታቸውን በፍቃዳቸው ትተውት ሳለ ከስነስርዓት ሕጉ ውጪ መልስ መቀበሉ አግባብነት ያለው ባለመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ፤ ባቀረብኩት ክስ መሰረት እንዲወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ሰበር ችሎቱ የአሁን አመልካች በስር ፍርድ ቤት የጠየቁት ዳኝነት ከተጠሪዎች ወላጆች ጋር በፈፀምኩት ውል መሰረት የተባለውን ቤት ከወላጆቻቸው ገዝቼ ተረክቤ ይዣለሁ ሆኖም ወላጆቻቸው ስም ሳያዘዋውሩልኝ ከዚህ አለም በሞት የተለዩ ስለሆነ ተጠሪዎች ባላቸው የወራሽነት መብት ግዴታም ስለሚወርሱ ስም ያዘዋውሩልኝ የሚል ሲሆን የስር ፍ/ቤቶች አለ የተባለው የሽያጭ ውል ረቂቅ ነው በማለት ድምዳሜ ላይ በመድረስ የሽያጭ ውሉ ሊፈርስ ይገባል አመልካችም በውሉ መነሻነት የከፈሉት ክፍያ ካለ ክስ አቅርበው መጠየቅ ይችላሉ በማለት የሰጡት ውሳኔ ከተጠየቀው ዳኝነት ውጪ በመውጣት ስለመሆን ያለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 182(2) እና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 31547 እና ሌሎች ተመሳሳይ መዝገቦች ላይ ከሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም አንፃር አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪዎችም በሰጡት መልስ የሥር ፍ/ቤት አመልካቾች በውሉ መሰረት እንዲፈፀምላቸው በጠየቁት ዳኝነት መሰረት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ያቀረቡትን ውል አውራሾቻችን በሕይወት እያሉ በሌላ መዝገብ በመ/ቁ.138864 ውሉን ክደው በመከራከራቸው መዝገቡ መዘጋቱን እንዲሁም

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ውሉ በሕግ አግባብ በአውራሾቻችን ያልተደረገና የማይፀና ውል መሆኑን እንዲሁም የውርስ ሀብቱ ሲጣራ አመልካች በመቃወም ያልተከራከሩ መሆኑን በማንሳት መከራከሪያ በማቅረባችን የስር ፍ/ቤቶች ማስረጃን መዝነው የሰጡት ውሳኔ በመሆኑ ሊፀና ይገባል በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካችም አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል እኛም ከግራ ቀኙ አቤቱታና መልስ እንዲሁም ለጉዳዩ ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች አንፃር መርምረነዋል፡፡ እንደመረመርነውም አመልካች በስር ፍ/ቤት በተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት ክስ አከራካሪውን ቤት ከተጠሪዎች አውራሽ ከሆኑት የተጠሪዎች እናትና አባት ጋር ህዳር 06 ቀን 2008 ዓ.ም በፈፀምነው ውል ሽጠውልኝ ብር 400,00.00 በመክፈል ቤቱን የተረከብኩ በመሆኑ የተጠሪዎች አውራሾች በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ ጽ/ቤት ቀርበው ስመ ሀብቱን ሊያዘዋውሩልኝ ተስማምተን የነበረ ቢሆንም ሳያዘዋውሩልኝ ህይወታቸው ያለፈ ስለሆነ ተጠሪዎች ስም ያዙሩልኝ በማለት የሚከራከሩ ሲሆን ተጠሪዎች በበኩላቸው አውራሾቻችን ፈጸሙ ስለተባለው የሽያጭ ውል አናውቅም አመልካች የቤት ሽያጭ ውል ነው በማለት ያቀረቡት ውል ወላጆቻችን ያልተዋዋሉት በሕግ አግባብ ያልተደረገ የመንደር ውል በመሆኑ ረቂቅ ውል ስለሆነ ሊያስገድደንም አይችልም በማለት የቤት ሽያጭ ዉል በአመልካች እና በአውራሾቻቸው መካከል ስለመደረጉ በግልጽ ክደዉ የተከራከሩ መሆኑን የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ በመሆኑም በአመልካች በተጠየቀዉ ዳኝነት መሠረት ተጠሪዎች ለመፈጸም የሚገደዱት በአመልካች እና በተጠሪዎች አውራሾች መካከል የተደረገ የቤት ሽያጭ ዉል መኖሩ ሲረጋገጥ በመሆኑ በእርግጥም በአመልካች እና በተጠሪዎች አውራሾች መካከል የተደረገ የቤት ሽያጭ ዉል መኖር አለመኖሩ በጭብጥነት ተጣርቶ እልባት ሊሰጥበት ይገባል፡፡ ጉዳዩን ለማስረዳት ሊቀርብ የሚገባዉ ማስረጃም ክርክሩ የማይንቀሳቀስ ንብረትን ለማስተላለፍ የተደረገን የሽያጭ ዉል የሚመለከት ከመሆኑ አኳያ የሚታይ ይሆናል፡፡

በመሰረቱ በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1723(1) ላይ የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን የሚመለከቱ ውሎች ሁሉ በጽሁፍ እና በሚገባ አኳኋን በፍርድ ቤት መዝገብ ወይም ውል ለመማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት መሆን እንዳለበት ተደንግጎ ይገኛል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 21448 እና በሌሎችም ተመሳሳይ መዝገቦች ላይም አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በዚህ አግባብ አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የአሁን አመልካች ከተጠሪዎች ወላጆች ጋር በ6/3/2008 ዓ/ም አድርገናል የሚሉት የቤት ሽያጭ ዉል በጽሑፍ የተደረገ መሆኑን የስር ፍርድ ቤቶች ክርክር የሚያመለክት ቢሆንም የአሁን ተጠሪዎች ይህ ዉል ስለመደረጉና ስለመኖሩ ክደው የተከራከሩ፣ እና ዉሉም የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1723 [1] ድንጋጌን መስፈርት አሟልቶ ያልተፈጸመ እስከሆነ ድረስ በሕግ ፊት የሚጸና የቤት ሽያጭ ዉል ተደርጓልና ሕጋዊ ተግባር አለ ለማለት የሚቻልበት የሕግ አግባብ የሌለ መሆኑን ገልጸው እስከተከራከሩ ድረስ ሰነዱ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1723(1) እና 1720 ድንጋጌዎች ይዘት አንጻር እንደረቂቅ ከሚቆጠር በስተቀር የዳኝነት ሚዛንን የሚደፋ የማስረጃነት ዋጋ የሚሰጠው አይደለም፡፡

ስለሆነም የአሁን አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተጠሪዎች ውሉ መደረጉን ክደው አልተከራከሩም በማለት ያቀረቡት ቅሬታ እና አመልካች ባልጠየቁበት ወይም ባልተነሳ ክርክር አመልካችም በውሉ መነሻነት የከፈሉት ክፍያ ካለ ክስ አቅርበው መጠየቅ ይችላሉ በማለት የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ከተጠየቀው ዳኝነት ውጪ በመውጣት ስለመሆን ያለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 182(2) እና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 31547 ከሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም አንጻር ለማጣራት የተያዘዉ ጭብጥ አመልካች ከተጠሪዎች ወላጆች ጋር የቤት ሽያጭ ውል አድርገናል ለዚህም ብር 400,000.00 ከፍያለሁ የተጠሪዎች አውራሾች ቤቱን ሰነዶች ማረጋገጫ እና ምዝገባ ጽህፈት ቤት ቀርበው ስም ሊያዞሩልኝ ተስማምተን ሳያዞሩልኝ ህይወታቸው ያለፈ ስለሆነ ተጠሪዎች ስም እንዲያዞሩልኝ ይወሰንልኝ የሚል ዳኝነት ጠይቀው የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት አለ የተባለው ውል በተጠሪዎች የተካደ ስለሆነ እና ውሉም ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1723(1) እና 1720 ድንጋጌዎች አንጻር እንደ ረቂቅ የሚቆጠር እና በህግ ፊት የማይጸና ነው በማለት ድምዳሜ ላይ ደርሶ አመልካች በውሉ መነሻነት ለተጠሪዎች ወላጆች የከፈሉት ክፍያ ካለ ከሰው መጠየቅ ይችላሉ በማለት የሰጠው ውሳኔ እና ይህንን ውሳኔ በማጽናት የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ትእዛዝ የፍ/ት/ብ/ህግ ቁጥር 1815(1)ን መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በስተቀር ባልተጠየቀ ዳኝነት የተሰጠ ውሳኔ ነው የሚያሰኝ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል የስር ፍርድ ቤቶች ተጠሪዎቸች የቤት ሽያጭ ዉል መደረጉንና መኖሩን ክደው የተከራከሩ በመሆኑ በሕግ ፊት የሚጸና ዉል የለም በማለት የሰጡት ዳኝነት በሕግ አግባብ ነዉ ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም ታከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ዉሳኔ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

1.የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ/234662 ላይ በቀን 2/9/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት የሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡

2.በዚህ ፍርድ ቤት ለተደረገዉ ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

3. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላላፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሠ/መ/ቁጥር 248877

ጥቅምት 29 ቀን 2017 ዓ/ም

ዳኞች ፡- እትመት አሠፋ

ደረጀ አያና

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

ብርሃኑ መንግሥቱ

አመልካቾች ፡- 1. ወ/ሮ አስካለ ካሳ ገ/ሥላሴ
2. ወ/ሮ ስሜነሽ ካሳ ገ/ሥላሴ } ቀረቡ
3. ወ/ሮ አየለች ካሳ ገ/ሥላሴ

ተጠሪ ፡- ወ/ሮ አልማዝ ሀብታሙ ገ/ሥላሴ -አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ጉዳዩ አባትነትን የመካድ ክስ ሊቀርብ የሚችልበትን አግባብ የሚመለከት ነዉ፡፡አመልካቾች በአሁን ተጠሪ እና በስር 2ኛ ተከሳሽ ወ/ሮ ጌጤ በየነ ወያ ላይ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ - አመልካቾች የሟች ወንድማችን አስር አለቃ ሀብታሙ ካሳ ገብረስላሴ ተተኪ ወራሾች መሆናችንን በፍርድ ቤት አስወስነናል፡፡በዚህ መሠረት አመልካቾች የሟች ወንድማችን ዉርስ እንዲጣራ አቤቱታ አቅርበን ዉርሱ በማጣራት ሂደት ላይ ተጠሪ የሟች አስርአለቃ ሀብታሙ ካሳ እና ከሚስታቸዉ የስር 2ኛ ተከሳሽ ሳይወለዱ ልጅ ነኝ በማለት ከሕግ-ዉጭ ከአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 1235/98 ላይ በቀን 17/08/1998 ዓ/ም

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የወራሽነት ማስረጃ መዉሰዳቸዉን አረጋግጠናል፡፡ሟች አስር አለቃ ሀብታሙ ካሳ ገ/ስላሴ በሕይወት ዘመናቸዉ ከ2ኛ ተከሳሽ ከወ/ሮ ጌጤ በየነ ወያ ጋር ጋብቻ መስርተዉ ይኖሩ የነበረ ቢሆንም ከአብራካቸዉ ልጅ አልወለዱም፡፡ወ/ሮ ጌጤ የተጠሪ እናት አይደሉም፡፡ ሆኖም 1ኛ ተጠሪ የሟች የአስር አለቃ ሀብታሙ ካሳ ባለቤት ከሆኑት ወ/ሮ ጌጤ በየነ ጋር የስጋ ዝምድና ስላላቸዉና ሟችም ስላሳደጓቸዉ ብቻ ልጅ ነኝ በማለት እንቅስቃሴ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ስለሆነም ተጠሪ የሟች አስር አለቃ ሀብታሙ ካሳ ገ/ስላሴ ልጅ አይደሉም ተብሎ ይወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ ለተሻሻለዉ ክስ በሰጡት መልስ - ተጠሪ የሟች አስር አለቃ ሀብታሙ ካሳ ልጅ ነኝ፡፡ልጅ ስላለመሆኔ አመልካቾች በቂ ማስረጃ አላቀረቡም፡፡2ኛ ተከሳሽ ወ/ሮ ጌጤ በአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ በመ/ቁጥር 1235/98 ላይ ቀርበዉ በሰጡት ምስክርነት ተጠሪን የወለድነዉ ሟች ሀብታሙ ካሳ እና እኔ ነን በማለት መስክረዋል፡፡ስለሆነም ከስር 2ኛ ተከሳሽ አልተወለደችም፤ የሟች ልጅ አይደለችም በማለት ያቀረቡት ክርክር የማስረጃ ድጋፍ የለዉም፡፡ክሱ አባትነትን መካድ እንጂ እናትነትን የመካድ ባለመሆኑ ከወ/ሮ ጌጤ ባልወለድ እንኳ የሟች አቶ ሀብታሙ ካሳ ልጅ የማልሆንበት አሳማኝ ምክንያት እና ማስረጃ ስላልቀረበ ክሱ ዉድቅ ሊሆን ይገባል፡፡አመልካቾች ሟች አቶ ሀብታሙ አባትነታቸዉን ስለመቀበላቸዉ አልካዱም፡፡ በስማቸዉ እጠራ እንደነበር አልካዱም፡፡ሟች ያመኑትንና የተቀበሉትን አባትነት ተቃዉመዉ የመካድ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል የሕግ ምክንያት የለም፡፡ ስለሆነም ክስ የቤተሰብ ሕጉን ተከትሎ ያልቀረበና የማስረጃ ድጋፍ የሌለዉ ስለሆነ ዉድቅ ይደረግልኝ በማለት መከራከራቸዉን ከስር ፍርድ ቤት መዝገብ ላይ ተመልክተናል፡፡

የስር 2ኛ ተከሳሽ በበኩላቸዉ አመልካቾች የ2ኛ ተከሳሽ ባለቤት የነበሩት የአስር አለቃ ሀብታሙ ካሳ እህቶች መሆናቸዉና ሟች አስር አለቃ ሀብታሙ ካሳም ከ2ኛ ተከሳሽ ጋር በጋብቻ ተሳስረን ለረጅም ዓመታት እስከ እለተ መቱ ድረስ አብረን ኖረናል፡፡2ኛ ተከሳሽና ሟች በጋብቻ ዉስጥም ሆነ ከጋብቻ ዉጭ የወለድነዉ ልጅ የለም፡፡በጋብቻችን ዘመን ልጅ ባለመዉለዳችን የወንድሜ የልጅ ልጅ የሆነችዉን የአሁን ተጠሪን ከሟች ባለቤቴ ጋር በጋራ ለማሳደግ ከገጠር አምጥተን አሁን የምትጠራበትን ስም በማዉጣት እና በሟች ባለቤቴ በአስር አለቃ ሀብታሙ ካሳ ስም እንድትጠራ በማድረግ አሳድገናታል፡፡ስለሆነም ተጠሪ ወንድሜ የልጅ ልጅ እንጅ ከእኔም ሆነ ከባለቤቴ አስር አለቃ ሀብታሙ ካሳ ስላልተወለደች በክሱ መሠረት ቢወሰን ተቃዉሞ የለኝም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ፍርድ ቤቱ ተጠሪ ከሟች አስር አለቃ ሀብታሙ ካሳ የተወለዱ ናቸዉ ወይስ አይደሉም የሚል ጭብጥ በመያዝ ምስክር ለመስማት በሂደት ላይ እያለ ወ/ሮ ድርቤ ዲንቃ ኤሌሞ የተባሉት ግለሰብ በቀን 25/09/2014ዓ/ም የተጻፈ አቤቱታ በማቅረብ የተጠሪ እናት እንደሆኑ እና ተጠሪን የወለዱትም ከስር 2ኛ ተከሳሽ የወንድም ልጅ ከአቶ ተሾመ ቶላ በ1975 ዓ/ም እንደሆነ፤እንዲሁም የስር 2ኛ ተከሳሽ ከሟች ባለቤታቸዉ ጋር ሆነዉ እንዳሳደጓት በመግለጽ በጉዳዩ ጣልቃ ገብተዉ እንዲከራከሩ እንዲፈቀድላቸዉ አመልክተዋል፡፡በዚህ አቤቱታ ላይ አመልካቾችና የስር 2ኛ ተከሳሽ በሰጡት አስተያየት አመልካቿ ጣልቃ ገብተዉ ቢከራከሩ እንደማይቃወሙ የገለጹ ሲሆን፤ ተጠሪ ደግሞ ጣልቃ ልግባ ባይ ተጠሪን በ4 ዓመቴ ለ2ኛ ተከሳሽና ባለቤታቸዉ እንዲያሳድጉኝ መስጠታቸዉን መግለጻቸዉ በሕግ ቋንቋ በጉዲፈቻ መስጠታቸዉን ያረጋግጣል፤ የመካድ ክስ ማቅረብ አይችሉም፤የተጠሪ እናት መሆናቸዉንና ከሟች አለመወለደን አላረጋገጡም በማለት አስተያየታቸዉን በመስጠት ተከራክረዋል፡፡ፍርድ ቤቱም በዚህ ረገድ የቀረበዉን ክርክር መርምሮ ወ/ሮ ድርቤ ዲንቃ ኤሌሞ በክርክሩ ጣልቃ ገብተዉ እንዲከራከሩ ፈቅዷል፡፡ሆኖም ወ/ሮ ድርቤ ዲንቃ ኤሌሞ ቀጣዩን የክርክር ሂደት ባለመከታተላቸዉ በሌሉበት ክርክሩ ተሰምቶ መወሰኑን የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ይዘት ያሳያል፡፡

በመቀጠል ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 300439 ላይ አስቀድሞ በተጠሪ የቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች በብይን ዉድቅ ካደረገ በኋላ ዋናዉን ጉዳይ በሚመለከት ግራ ቀኙ ያሰሙትን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ በቀን 23/12/2014ዓ/ም በሰጠዉ ፍርድ - በተሻሻለዉ የፌዴራል ቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 213/1992 አንቀጽ 154 መሠረት አባትነት ወይም እናትነት በመርህ ደረጃ በልደት ምስክር ወረቀት ሊረጋገጥ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡የልደት ምስክር ወረቀት ከሌለ የልጅነት ሁኔታ መኖሩን በማስረዳት ልጅነት ማረጋገጥ እንደሚቻል በቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 155 እና 156 ስር ተደንግጓል፡፡ነገር ግን ይህ ማስረጃ በሌላ ተቃራኒ ማስረጃ ሊስተባበል እንደሚችል በሰ/መ/ቁጥር 33440 ላይ የሕግ ትርጉም ተሰጥቷል፡፡ የልጅነት ሁኔታ አለ የሚባለዉ አንድ ሰዉ በምኖርበት ማህበረሰብ ዘንድ የእርሱ ልጅ ወይም የእርሷ ልጅ ነዉ እየተባለ የሚገመት ሲሆን ነዉ፡፡ተጠሪ በክርክራቸዉ እንደገለጹትና በማስረጃነት ባቀረቡት ሰነዶች ማለትም ልጅነት በቀበሌ ቅጽ እና በመስሪያ ቤት ፎርም ላይ ስም በመሙላት ሊረጋገጥ አይችልም፡፡ተጠሪ የልደት ምስክር ወረቀት ያወጡት ሟች ከሞቱ በኋላ በመሆኑ ፤የልደት ምስክር ወረቀት የሚሰጠዉ የነዋሪነት መታወቂያ ካርድ በማየት እንጂ ወላጆችን ጠርቶ አናግሮ አስፈላጊ ማጣሪያ በማድረግ ስላልሆነ ተጠሪ በማስረጃነት ያቀረቡትን የልደት ምስክር ወረቀት አላመነበትም፡፡ስለሆነም የአመልካቾች ምስክሮች

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

እና ጣልቃ ገብ የተጠሪ ወላጅ አባት አቶ ተሾመ ቶላ መሆኑን ያረጋገጡ በመሆኑና ይህንን የሚያስተባብል ማስረጃ በተጠሪ ስላልቀረበ፤ እንዲሁም አስቀድሞ የጉዲፈቻ ልጅ ነኝ በማለት ስላልተከራከሩና የጉዲፈቻ ልጅ ስለመሆናቸዉ ያላስረዱ በመሆኑ የሟች አስር አለቃ ሀብታሙ ካሳ ልጅ አይደሉም በማለት ፍርድ ሰጥቷል።

በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ተጠሪ ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዉ ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 296421 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 06/04/2015 ዓ/ም በሰጠዉ የፍርድ ዉሳኔ የመካድ ክስ ለማቅረብ ማስፈቀድ የሚገባ ለመሆኑ በቤተሰብ ሕጉ ከአንቀጽ 163-166 ተደንግጓል፡፡የመካድ ክስ የሚያቀርብ አካል በሕጉ አንቀጽ 171/2 መሠረት ፍርድ ቤቱ ክሱን ለመቀበል በቂና አሳማኝ ከሚሆን መረጃ የሚመነጭ በህሊና ግምት ወይም ከባድ ምልክት መኖሩን ማስረዳት ይኖርበታል፡፡ሟች በህይወት በነበሩበት ወቅት ተጠሪን ልጄ ናት ብለዉ በቀበሌ ማህደር እንዲሁም በመስሪያ ቤታቸዉ በማስመዝገብ ልጅነቷን የተቀበሉ መሆኑን ከመጡት ማስረጃዎች የምንረዳዉ ሲሆን ሟች በህይወት እያሉ ተጠሪን ልጄ ብለዉ የተቀበሏቸዉ በመሆኑ ሟች የተቀበሏቸዉን ልጅ አመልካቾች በእርሳቸዉ እግር ተተክተዉ የመካድ ክስ ሊያቀርቡ አይችሉም፡፡የመካድ ክስ ማቅረብ የሚችል ሰዉ ሟቹ ልጄ ነዉ ብሎ ያተቀበለዉን ልጅ እንጂ ተቀብሎ ያሳደገዉን ልጅ ልጅ አይደለም በማለት የመካድ ክስ ለማቅረብ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 177/3 መሠረት መብት አላቸዉ በማለት መፍቀድ የሕጉን ዓላማ መጣስ ይሆናል፡፡በሌላ በኩል የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ያቀረቡትን የይርጋ መቃወሚያ ዉድቅ ያደረገዉ ተጠሪ የልደት ምስክር ወረቀት ያወጡት በ2014ዓ/ም ስለሆነ ይርጋዉ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ስለሚቆጠር የአመልካቾች መብት በይርጋ ቀሪ አልሆነም በማለት ሲሆን አመልካቾች የመካድ ክስ ለማቅረብ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 177 መሠረት መብት ያላቸዉ ቢሆንም አመልካቾች ክሱን ያቀረቡት ሟች ከሞቱ ከ15 ዓመት በኋላ ነዉ፡፡ እንዲሁም ሟች ተጠሪን ከወለዱ ከ39 ዓመት በኋላ ሲሆን ሟች በሕጉ አንቀጽ 176/1 ስር በተመለከተዉ ጊዜ ዉስጥ ያልተጠቀሙና የመካድ ክስ ሊቀርብ የሚገባዉ ልጅ መወለዱን ካወቁበት ወይም ማወቅ ከሚገባዉ ጊዜ ጀምሮ በ180 ቀናት ዉስጥ በመሆኑ የሟች መብት በይርጋ ስለታገደ የአመልካቾችም የመካድ ክስ የማቅረብ መብት በይርጋ ቀሪ ሆኗል፡፡ ስለሆነም አመልካቾች የመካድ ክስ እንዲያቀርቡ ሊፈቀድላቸዉ አይገባም፤ የአመልካቾች ክስ የማቅረብ መብት በይርጋ የታገደ ነዉ በማለት የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ የሟች ልጅ አይደሉም ሲል የሰጠዉን ዉሳኔ ሽሯል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በመቀጠል አመልካቾች በዉሳኔዉ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ቢሆንም በመ/ቁጥር 240136 ላይ በቀን 24/08/2015 ዓ/ም በተሰጠ ትእዛዝ ዉሳኔዉ ጉድለት የለበትም ተብሎ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ተሠርዞባቸዋል፡፡

አመልካቾች ለዚህ ሰበር ችሎት በቀን 07/10/2015 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት - የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የልደት ምስክር ወረቀት የወጣዉ በጥቅምት 2014 ዓ/ም መሆኑን፤ሟች የፖሊስ አባል ስለነበሩ ለህክምና እርዳታ ተጠሪን ማስመዝገቡና ቀበሌ እንደቤተሰብ ማስመዝገቡ የሚስተባበል ማስረጃ እንደሆነ፤ የቤተሰብ ሕጉን አንቀጽ 167፣174 እና 179 ስር የተደነገገዉን እና በሰ/መ/ቁጥር 999554 ላይ የተሰጠዉን የሕግ ትርጉም መሠረት በማድረግ የሰጠዉ ዉሳኔ ትክክል ሆኖ እያለ ሟች የተጠሪን ስም በመስሪያ ቤቱ እና በቀበሌ ነዋሪነት ማህደር ላይ በማስመዝገቡ ብቻ ይህን ያደረገዉ አባት ነኝ ከሚል ስሜትና መንፈስ በመነጨ ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበት ልጅነቷን ተቀብሏል፤ መካድ አይቻልም በማለት መወሰኑ በሰ/መ/ቁጥር 32130 ላይ የተሰጠዉን የሕግ ትርጉም የሚቃረን ነዉ፡፡ ዉሳኔዉ በሰ/መ/ቁጥር 33440 ላይ የልደት ምስክር ወረቀት ማስተባበል እንደሚቻል እና በአሳዳጊ መጠራት የአባትነት ግምት እንደማይፈጥር ተገልጾ በሰ/መ/ቁጥር 95995 እና 87420 ላይ የተሰጠዉን ዉሳኔ የሚቃረን ነዉ፡፡ዉሳኔዉ የተጠሪ እናትና አባት አሁንም በህይወት እንዳሉ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠዉን ያላገናዘበ ነዉ፡፡ ይርጋዉ መቆጠር ያለበት በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1846 እና በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 176/1 መሠረት አመልካቾች ፍሬ ነገሩ መኖሩን ካወቅንበትና በመብታችን መስራት ከምንችለበት ከጥቅምት 2014ዓ/ም ጀምሮ ሊሆን ይገባል፡፡ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ሲታይ መብታችን በይርጋ ቀሪ ባልሆነበት የአመልካቾች መብት በይርጋ ቀሪ የሆነ ነዉ ሲል የሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ተሽሮ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዉሳኔ ይጽናልን በማለት አመልክተዋል፡፡

ችሎቱ አቤቱታዉን መርምሮ 1) ተጠሪ በታወቀ ግንኙነት ዉስጥ መወለዳቸዉ ሳይረጋገጥ የአመልካቾች ክስ የመካድ ክስ ነዉ ተብሎ መወሰኑ ሕግን መሠረት ያደረገ ነዉ ወይ? 2) የአመልካቾች አዉራሽ ድርጊት ልጅነትን ስለመቀበል በቤተሰብ ሕጉ የተመለከተዉን ሥርዓት የተከተለና ሕጋዊ ዉጤት ያለዉ ነዉ ወይ? የሚሉ ጭብጦችን ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲሰጡ አዝዟል፡፡

ተጠሪ በቀን 25/06/2016ዓ/ም በተጻፈ መልሳቸዉ - አመልካቾች ለስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ ላይ በግልጽ ክሳቸዉ የመካድ ክስ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡የመካድ ክስ ለማቅረብ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

እንዲፈቀድላቸዉ ማስፈቀጃ አቅርበዉ ተጠሪ ሊፈቀድላቸዉ አይገባም በማለት ያቀረብኩትን መቃወሚያ የስር ፍርድ ቤት ዉድቅ በማድረግ የመካድ ክስ እንዲያቀርቡ ፈቅዶላቸዉ የቀረበ የመካድ ክስ በመሆኑ ክርክሩም መመራት ያለበት ያቀረቡትን የመካድ ክስ መሰረት በማድረግ በመሆኑ ክሱ የመካድ ክስ ነዉ ተብሎ በመወሰኑ የተፈጸመ ስህተት የለም፡፡ሟች ሀብታሙ ካሳ በህይወት እያሉ ተጠሪ ልጃቸዉ ስለመሆኔ በተለያዩ የመንግሥት ተቋማትና በሚሰሩበት መስሪያ ቤት ጭምር አባትነታቸዉን ተቀብለዉ በልጅነት እንዳስመዘገቡኝ በማስረጃ አስረድቻለሁ፡፡ከዚህም በተጨማሪ ሟች የክብር መዝገብ ሹምን ሥራ ተክቶ በሚሠራዉ ቀበሌ ባላቸዉ ማህደር ዉስጥ በሚገኝ ቅጽ ላይ እና በፖሊስ ሠራዊት መስሪያ ቤት የቤተሰብ መመዝገቢያ ማህደር በልጅነት እንዳስመዘገቡኝ ተረጋግጧል፡፡ይህ ማስረጃ ሀሰተኛ ነዉ በሚል የቀረበ ክርክር የለም፡፡ሟች አባትነታቸዉን ተቀብለዉ የሰጡትን ቃል አመልካቾች የመሻር መብት የላቸዉም፡፡ሟች በህይወት ቢኖሩ ኖሩ በዚህ መልኩ የተቀበሉትን ልጅነት በቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 140/1 ስር በተደነገገዉ መሠረት መሻር ስለማይችሉ ለሟች እንኳ ሊፈቀድ የማይችል መብት ለአመልካቾች ሊፈቀድ ስለማይችል ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ ተገቢ ነዉ፡፡አመልካቾች የመካድ ክስ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 176/1 መሠረት በ180 ቀናት ዉስጥ ስላላቀረቡ ክስ የማቅረብ መብታቸዉ በይርጋ የታገደ ነዉ መባሉም ተገቢ ነዉ፡፡ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 171/2 ስር የተደነገጉት ሁኔታዎች ባልተሟሉበት በሟች እና በሚስታቸዉ በወ/ሮ ጌጤ በየነ መካከል በነበረዉ ጋብቻ ዉስጥ ልጅ አልተወለደም የሚል ምክንያት መሠረት በማድረግ ሟች ተጠሪን ሊወልዱ የማይችሉበት ምክንያት ሳይቀርብ የስር ፍርድ ቤት አመልካቾች የመካድ ክስ እንዲያቀርቡ መፍቀዱ ስህተት ነዉ፡፡ የጣልቃ ገብ ማንነት በአግባቡ በማስረጃ አልተረጋገጠም፡፡ጣልቃ ገብ አቤቱታቸዉን የሚደግፍ ማስረጃም አላቀረቡም፡፡የጉዲፈቻ ጉዳይ የተነሳዉ በጣልቃ ገብ አመልካች እንጂ በተጠሪ አይደለም፡፡የልደት ምስክር ወረቀት ከሟች ሞት በኋላ መዉጣቱም ልጅነትን ሊያረጋግጥ አይችልም የሚባልበት የሕግ መሠረት የለም፡፡ስለሆነም በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች የተሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢ ነዉ ተብሎ ይጽናልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካቾችም የመልስ መልሳቸዉን በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ከላይ አጠር ባለ መልኩ የተገለጸዉ የግራ ቀኙን ክርክር፣ በይግባኝ ሰሚዉ ችሎትና በስር በፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት የሚመለከት ሲሆን እኛም ከፍ ሲል በተመለከተዉ መሠረት የተያዙትን ጭብጦች መሠረት በማድረግ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የሕግ

ስህተት መፈጸም አለመፈጸሙን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

በመጀመሪያም ተጠሪ በሕግ በታወቀ ግንኙነት ዉስጥ መወለዳቸዉ ሳይረጋገጥ የአመልካቾች ክስ የመካድ ክስ ነዉ ተብሎ መወሰኑ ሕግን መሠረት ያደረገ ነዉ ወይ? በሚል የተያዘዉን ጭብጥ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነዉም አመልካቾች የሟች አስር አለቃ ሀብታሙ ካሳ እህቶች እንደሆኑ አላከራከረም፡፡ እንዲሁም አመልካቾች የሟቹ ተተኪ ወራሽ መሆናቸዉን በፍርድ ቤት ማስወሰናቸዉ በስር ፍርድ ቤቶች በማስረጃ የተረጋገጠ ነዉ፡፡አመልካቾች በተጠሪ እና በስር 2ኛ ተከሳሽ ወ/ሮ ጌጤ ላይ የመሠረቱት ክስ ከርዕሱ ጀምሮ ይዘቱ የመካድ ክስ ነዉ በሚል የቀረበ መሆኑን በስር ፍርድ ቤት መዝገብ ዉስጥ ካለዉ የክስ ማመልከቻ ይዘት ላይ ተገንዝበናል፡፡አመልካቾች በተጠሪ ላይ ክስ እንዲመሰርቱ መነሻ የሆናቸዉ ምክንያት ተጠሪ የሟች ልጅ እንደሆኑ ገልጸዉ ከሕግ አግባብ ዉጭ ከአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 1235/98 ላይ በቀን 17/08/1998ዓ/ም የወራሽነት ማስረጃ መዉሰዳቸዉን የሟች ዉርስ በሚጣራበት ሂደት ተገንዝበናል የሚል ነዉ፡፡ከዚህ በሻገር አመልካቾች ለመሠረቱት የመካድ ክስ የክስ ምክንያት አድርገዉ የጠቀሱትና የጠየቁት ዳኝነት ሟች በሕይወት ዘመናቸዉ ከስር 2ኛ ተከሳሽ ወ/ሮ ጌጤ በየነ ጋር በጋብቻ ተሳስረዉ ሲኖሩ ከአብራካቸዉ ልጅ ሳይወልዱ፤ ወ/ሮ ጌጤ በየነም የተጠሪ እናት ባልሆኑበት ከሕግ-ወጭ በሆነ አግባብ የወራሽነት ማስረጃ ስለወሰዱ ልጅ አይደሉም ተብሎ ይወሰንልን በሚል ነዉ፡፡ተጠሪ ደግሞ ለአመልካቾች የመካድ ክስ እንዲያቀርቡ ሊፈቀድላቸዉ እንደማይገባ፤ክሱን ለማቅረብ መብት እንደሌላቸዉ፤የአመልካቾች ክስ በይርጋ የታገደ እንደሆነ በመግለጽ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማቅረብ ከመከራከራቸዉም በተጨማሪ እናታቸዉ ማን እንደሆኑ ሳይገልጹ ወይም የስር 2ኛ ተከሳሽ ወ/ሮ ጌጤ በየነ እናቴ ናቸዉ የሚል ግልጽ ክርክር ሳያቀርቡ፤ እንዲሁም ሟች አስር አለቃ ሀብታሙ ካሳ ከሌላ ሴት ጋር በነበራቸዉ የታወቀ ግንኙነት እንደወለዷቸዉ ሳይገልጹ ሟች በተለያዩ መስሪያ ቤቶች አባት መሆናቸዉን በመግለጽ ስላስመዘገቡኝ ሟች አባታቸዉ እንደሆኑና የተሰጣቸዉም የወራሽነት ማስረጃ በአግባቡ ተረጋግጦ የተሰጠ እንደሆነ በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡በሌላ በኩል የስር 2ኛ ተከሳሽ ወ/ሮ ጌጤ በየነ ሟች እስከሞቱበት ድረስ ከሟች ጋር ልጅ እንዳልወለዱና ተጠሪን ከሟች ባለቤታቸዉ ጋር ቢያሳድጓቸዉም የወንድማቸዉ ልጅ ልጅ እንደሆኑ በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡

በዚህ መልኩ ከቀረበዉ ክርክርና የስር ፍርድ ቤቶችም ከላይ በተገለጸዉ መሠረት ካረጋገጡት ፍሬ ነገሮች ማረጋገጥ የቻልነዉ በሟች አስር አለቃ ሀብታሙ ካሳ እና በስር 2ኛ ተከሳሽ ወ/ሮ ጌጤ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በየነ መካከል ሟች አስከሞቱበት ጊዜ ድረስ ጸንቶ የቆየ ጋብቻ እንደነበር እና ወ/ሮ ጌጤ በየነ የተጠሪ እናት እንዳልሆኑ ነዉ። በተጨማሪም በተጠሪ በኩል ሟች ከሌላ ሴት ጋር በነበራቸዉ ጋብቻ ወይም እንደባልና ሚስት በመሆን ከሌላ ሴት ጋር ሲኖሩ ወይም ደግሞ ሟች ከእናታቸዉ ጋር በሕግ የታወቀ ግንኙነት ሳይኖራቸዉ በሕግ በተመለከተዉ የእርግዝና ጊዜ ቀጣይነት ባለዉ ሁኔታ በግብረ ሥጋ ግንኙነት አብረዉ ሲኖሩ ወልደዉኛል በሚል ያቀረቡት ግልጽ ክርክር አለመኖሩን ተገንዝበናል፡፡

በተሻሻለዉ የፌዴራል ቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 *ስለመወለድ* በሚደነግገዉ ምዕራፍ ዘጠኝ ስር ባሉት ድንጋጌዎች ላይ አባትነት የሚረጋገጠዉ በሦስት መንገዶች እንደሆነ ተመልክቷል። አንደኛዉ መንገድ በዚሁ ምዕራፍ ክፍል ንዑስ ክፍል ሁለት ስር ባሉ ድንጋጌዎች እንደተመለከተዉ አባትነት በሕግ ግምት የሚታወቅበት (Presumption of Paternity) ሲሆን፤ሁለተኛዉ መንገድ ደግሞ አባትየዉ በዚሁ ምዕራፍ ንዑስ ክፍል ሦስት ስር ባሉ ድንጋጌዎች መሠረት ልጁን ልጄ ነዉ ሲል በመቀበል (Acknowledgement of Paternity) ሆኖ ሦስተኛዉና የመጨረሻዉ ደግሞ በዚሁ ምዕራፍ ንዑስ ክፍል አራት ስር ባሉ ድንጋጌዎች መሠረት አባትነት በፍርድ ቤት ዉሳኔ የሚታወቅበት (Ascertainment of Paternity by Judicial Declaration*)* ነዉ፡፡

የቤተሰብ ሕጉ አባትነትን በሕግ ግምት የሚታወቅበትን መንገድ በተመለከተ የያዘዉን አቋም የያን እንደሆነ - የዚህ ዓይነት የሕግ ግምት የሚወስደው ልጁ በሚፀነስበት ወይም በሚወለድበት ጊዜ በልጁ እናት እና በአንድ ወንድ መካከል በሕግ የታወቀ ግኑኝነት መኖሩ ሲረጋገጥ እንደሆነ፤ በዚህ መልኩ በሕግ እውቅና የተሰጠው ግንኙነት የሚባለዉም ጋብቻ እና ጋብቻ ሳይኖር እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኝነት ብቻ ስለመሆኑ ከቤተሰብ ሕጉ አንቀፅ 126 እና 130 ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህንንም አባትነት የሚታወቅበትን የሕግ ግምት መቃወም የሚቻለዉ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 167 እና ተከታዮቹ በተደነገገዉ መሠረት የመካድ ክስ በማቅረብ ብቻ ነዉ። በዚህ መሠረት በሕጉ በአባት በኩል ያለዉን መወለድ መቃወም የሚቻለዉ በፍርድ ቤት ፈቃድ እንደሆነ፤ለመቃወም መብት ስለአላቸዉ ሰዎች ማንነት ፤ክስ ስለሚቀርብበት ጊዜ እና ግምቱ ስለሚስተባበልበት አግባብ በሕጉ በጠባቡ ተደንግጓል።በሕጉ በዚህ መልኩ በጠባቡ የተደነገገዉ በሕግ እዉቅና የተሰጣቸዉ ግንኙነቶች የቤተሰብ መሠረቶች በመሆናቸዉ እና ለእነዚህ ሕጋዊ ግንኙነቶችና በግንኙነቱ ለተወለዱ ልጆች መብቶች ጥበቃ በማድረግ ደህንነታቸዉንና ዘላቂነታቸዉ ለማረጋገጥ ብሎም የቤተሰብ ግንኙነት ሰላማዊ እንዲሆን ለማድረግ ነዉ፡፡ በመሆኑም ባልየዉ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ወይም ከእናትየዋ ጋር አብሮ የሚኖር ሰዉ የልጁ አባት አይደለም ተብሎ ሊወሰን የሚችለዉ በዚህ የሕግ አግባብ የመካድ ክስ የቀረበ እንደሆነና በዚህ ሕግ አንቀጽ 167–174 መሰረት ተጣርቶ የሕግ ግምቱ ሲስተባበል ብቻ ነዉ ።

ከላይ እንደተገለጸዉ አመልካቾች ሟች ልጅ አልወለዱም፤ተጠሪ ሟች ከስር 2ኛ ተከሳሽ ወ/ሮ ጌጤ በየነ ጋር በጋብቻ ዉስጥ በነበሩበት ጊዜ ስላልተወለዱ ልጅ አይደሉም በማለት ተከራክረዋል። ተጠሪ በበኩላቸዉ ከሟች ጋር የታወቀ የጋብቻ ግንኙነት ከነበራቸዉ ከስር 2ኛ ተከሳሽ ወ/ሮ ጌጤ በየነ ተወልጃለሁ በማለት በግልጽ ያቀረቡት ክርክር የለም። በተጨማሪም ወ/ሮ ጌጤ በየነ በስር ፍርድ ቤት ተከሳሽ በመሆን ቀርበዉ ተጠሪን እንዳልወለዱን ከሟች ጋር በጋብቻ ዉስጥ በቆየበት ዘመን ሟችም ሆነ እርሳቸዉ ልጅ እንዳልወለዱ አስረድተዋል። እንዲሁም ተጠሪ ሟች ከሌላ ሴት ጋር እንደባልና ሚስት አብረዉ ሲኖሩ የተጸነሱ ወይም የተወለዱ ስለመሆኑ በመግለጽ ያቀረቡት ክርክር የለም።በመሆኑም ሟች አስር አለቃ ሀብታሙ ካሳ የተጠሪ አባት ናቸዉ የሚል የሕግ ግምት መዉሰድ ስለማይቻል ተጠሪ በሕግ በታወቁ ግንኙነቶች አለመወለዳቸዉ በመረጋገጡ በአባትነት የሕግ ግምት ተጠቃሚ ሊሆኑ አይችሉም።ይህ በመሆኑም አመልካቾችም በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 167 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሠረት የመካድ ክስ ለማቅረብ አይገደዱም።

ከላይ እንደተገለጸዉ አመልካቾች የመካድ ክስ ለማቅረብ የማይገደዱ ከሆነ የክስ ማመልከቻቸዉ በአባት በኩል ያለዉን መወለድ መካድን የሚመለከት ይዘት ያለዉ ቢሆንም በጉዳዩ ላይ ዉሳኔ ለሚሻዉ ዋነኛ ነጥብ ተፈጻሚ የሚሆነዉን የሕጉን ክፍልና ድንጋጌ ለይቶና ተግባራዊ በማድረግ ዉሳኔ የመስጠት ኃላፊነት የፍርድ ቤቶች እንደመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ከዚህ አኳያ ኃላፊነታቸዉን በአግባቡ መወጣት ይኖርባቸዋል። አመልካቾች የመካድ ክስ ለማቅረብ የማይገደዱ እስከሆነ ድረስ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 167 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሠረት የመካድ ክስ ለማቅረብ የፍርድ ቤት ፈቃድ መጠየቅ አይጠበቅባቸዉም፤ሟች የተጠሪ አባት እንደሆኑ የሕግ ግምት ሊወሰድ ስለማይችል የሕግ ግምቱን አመልካቾች ለማስተባበል አይገደዱም፤እንዲሁም የግራ ቀኙ ክርክር አባትነትን በመካድ የሕግ ማዕቀፍ ዉስጥ የሚታይ ባለመሆኑ በሕጉ አንቀጽ 176/1 ስር ክስ ስለሚቀርብበት የይርጋ ጊዜ የተደነገገዉ በያዝነዉ ጉዳይ ተፈጻሚ አይሆንም።በመሆኑም የስር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አመልካቾች ተጠሪ በሕግ በታወቀ ግንኙነት ዉስጥ ከሟች አስር አለቃ ሀብታሙ ካሳ ባልተወለዱበት የሟች የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ እንደሆኑ በመግለጽ ከሕግ አግባብ ዉጭ ማስረጃ እንደወሰዱ በመግለጽ በክሳቸዉ ከገለጹት የክስ ምክንያትና ከጠየቁት ዳኝነት አንጻር ማየት ሲገባቸዉ ክርክሩን አባትነትን ስለመካድ በሚመለከቱ ድንጋጌዎች መሠረት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

መርምረዉ መወሰኑና ይህንንም ሲህተት ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት አለማረሙ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡

በመቀጠል የአመልካቾች አዉራሽ ድርጊት የተጠሪን ልጅነት ስለመቀበል በቤተሰብ ሕጉ የተመለከተዉን ሥርዓት የተከተለና ሕጋዊ ዉጤት ያለዉ ነዉ ወይ? በሚል የያዝነዉን ሁለተኛዉን ጭብጥ መርምረናል፡፡ ተጠሪ በሕግ በሚታወቅ ጋብቻ ዉስጥ ወይም እንደባልና ሚስት አይነት ግንኙነት ወይም ከሁለቱ በአንዱ በሕግ በሚታወቅ ግንኙነት ዉስጥ እንዳልተወለዱ ከላይ በተገለጸዉ መሠረት ተረጋግጧል፡፡ እንዲሁም የሟች ልጅ እንደሆኑ በመግለጽ ከአዲስ አበባ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሟች የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ስለመሆናቸዉ የወሰዱት ማስረጃ ጸንቶ ሊቀጥል የሚችለዉ ሟች ልጄ ናቸዉ በማለት የተቀበሏቸዉ ስለመሆኑ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 131 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሠረት እና በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 143 እና ተከታዮቹ መሠሰረት አባትነት በፍርድ ቤት ዉሳኔ የሚታወቅበት ሁኔታዎች መኖራቸዉን በመግለጽ በማስረጃ የተደገፈ ክርክር ሲያቀርቡ ነዉ፡፡ ሰዎች የወራሽነት ማስረጃ የሚወስዱ መብት ለማቋቋም በማሰብ እንደመሆኑ ይህንን ማስረጃ በመጠቀም በሚደረግ ተግባራት የሦስተኛ ወገኖች መብቶች ሊነካ የሚችልበት ሁኔታ ሊፈጠር እንደሚችል ከግምት በማስገባት ማስረጃዉን የሚሰጠዉ ፍርድ ቤትም የወራሽነት ማስረጃ ሲሰጥ ጠያቂዎቹ ከሟች ጋር አለን የሚሉትን ግንኙነት በተገቢዉ ማስረጃ እንዲያረጋግጡ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ በዚህ መሠረት ልጅነትን ስለመቀበል በቤተሰብ ሕጉ ከአንቀጽ 131-142 ስር እንደተደነገገዉ በሕግ በታወቀ ግንኙነት ያልተወለደዉን ልጅ ልጄ ነዉ በማለት መቀበል የሚቻለዉ በእነዚህ ድንጋጌዎች ላይ በተዘረጋዉ ሥርዓት መሠረት ሆኖ ልጅነትን መቀበል የሚችለዉ ሰዉ ደግሞ የልጁ የተፈጥሮ አባት ነኝ የሚል ሰዉ ነዉ፡፡ይህንንም በተለይም ከሕጉ አንቀጽ 136/1 ስር *የልጁ እናት የተቀባዩን አባትነት እዉነትነት ያለዉ መሆኑን ካላመነች በስተቀር* አባት ልጄ ነዉ ሲል የሚሰጠዉ ቃል በሕግ ፊት ዉጤት እንደማይኖረዉ በአስገዳጅነት ከተደነገገዉ መገንዘብ ይቻላል፡፡በያዝነዉ ጉዳይ ተጠሪ በሕግ ባልታወቀ ግንኙነት ሟች ከማን እንደወለዷቸዉ እና አባት ነኝ ብለዉ እንደተቀበሏቸዉ በመግለጽ ያሰሙት ግልጽ ክርክር ካለመኖሩም በተጨማሪ በሕጉ በተደነገገዉ አግባብ ሟች ልጄ ናት በማለት ተቀብሏቸዋል የሚያስብል ማስረጃ አልቀረቡም፡፡

በተጨማሪም በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 131 ስር በተመለከተዉ ሥርዓት መሠረት ልጅነት መቀበል የሚቻለዉ አንድ ሰዉ የክብር መዝገብ ሹም ፊት በመቅረብ አባት መሆኑን በመግለጽ በሚሰጠዉ ቃል ወይም በጽሁፍ በሚያደርገዉ ኑዛዜ ወይም በሌላ በማናቸዉም ሥልጣን በተሰጠዉ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ዉሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ባለሥልጣን በተረጋገጠ ሰነድ አማካይነት አባት መሆኑን በመግለጽ ልጅነቱን ሲቀበል ነዉ፡፡እንዲሁም አባትነት ወይም በእናትነት በኩል የአንድ ሰዉ ልጅነት የእገሌ ልጅ ነዉ የሚል የልደት ምስክር ወረቀት በማቅረብ ማረጋገጥ እንደሚቻል በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 154 ስር ተደንግጓል፡፡በተያዘዉ ጉዳይ ተጠሪ ሚች አባታቸዉ እንደሆኑ የስር 2ኛ ተከሳሽ ወ/ሮ ጌጤ በየነ እናታቸዉ እንደሆኑ የተገለጸበትን የልደት ምስክር ወረቀት በማስረጃነት ያቀረቡ ቢሆንም ይህንን የልደት ምስክር ወረቀት የወሰዱት ሚች ከሞቱ ከረጅም ዓመታት በኂላ መሆኑን የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከማስረጃዉ ላይ አረጋግጧል፡፡እኛም ከስር ፍርድ ቤት መዝገብ ይህንኑ ተገንዝበናል፡፡በዚህ አግባብ ከተረጋገጠዉ ፍሬ ነገር መገንዘብ የሚቻለዉ በሕጉ አንቀጽ 131 ስር በተደነገገዉ ሥርዓት መሠረት ሚች በክብር መዝገብ ሹም ፊት በአካል በመቅረብ የተጠሪን ልጅነት አለመቀበላቸዉን ነዉ፡፡ሌላዉ በማስረጃነት የቀረቡት ሚች በፖሊስ መስሪያ ቤት እና በቀበሌ ጽ/ቤት ባላቸዉ ማህደር በልጅነት አስመዝገበዉኛል የሚል ነዉ፡፡ ሆኖም የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ማስረጃዎቹን መርምሮ ልጅነት በቀበሌ ቅጽ እና በመስሪያ ቤት ፎርም ላይ በመሙላት አይረጋገጥም በሚል የደረሰበትን ድምዳሜ የስር 2ኛ ተከሳሽ ወ/ሮ ጌጤ በየነ ተጠሪን የወለዱት የወንድማቸዉ ልጅ እንደሆኑና ሚችም ሆኑ እርሳቸዉ ተጠሪን ከገጠር አምጥተዉ ከማሳደግ ባለፈ እንዳልወለዷቸዉ ካስረዱት ጋር ተገናዝቦ ሲታይ ሚች በተጠቀሱት መስሪያ ቤቶች ላይ በተጠሪ አባት ስም ቦታ ላይ ስማቸዉን ያስመዘገቡት ተጠሪን ከመርዳት መንፈስ ነዉ ከሚባል በስተቀር ሚች አባት ነኝ በሚል መንፈስ የተጠሪን ልጅነት ለመቀበል የፈጸሙት ድርጊት ነዉ ብሎ ለደምደም የሚያስችል የሚያበቁ ማስረጃዎች አይደሉም፡፡እንዲህ አይነት ተግባር መፈጸም ልጅነትን እንደመቀበል እንደማይቆጠር ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 32130(ቅጽ 5) ላይ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡በተጨማሪም እነዚህ ማስረጃዎች በሚች እና በተጠሪ እናት መካከል ሚች ተጠሪን እንዲወልዱ ያደረገ ግንኙነት መኖሩን የሚያሳዩ ሰነዶች አይደሉም፡፡ስለሆነም ከዚህም አኳያ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሚች የተጠሪን ልጅነት ተቀብለዋል ተብሎ የተደረሰበት ድምዳሜ የማስረጃ ምዘና ምርህ እና የሕግ አተገባበር ጉድለት ያለበት ሆኖ እያለ በይግባኝ ሰሚዉ ችሎት አለመታረሙ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡

እንዲሁም ተጠሪ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 143 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ስር አባትነት በፍርድ ቤት ዉሳኔ የሚታወቅበት ሁኔታዎች መኖራቸዉን መሠረት በማድረግም ሆነ ተወላጅነታቸዉ እንዲረጋገጥ በሕጉ አንቀጽ 158 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሠረት ፍርድ ቤትን በማስፈቀድ ያሰጡት የልጅነት ዉሳኔ ስለመኖሩ በመግለጽ ያልተከራከሩና ዉሳኔዉንም በማስረጃነት ያላቀረቡ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በመሆኑ የሟች አስር አለቃ ሀብታሙ ካሳ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ናቸዉ ተብሎ የተሰጣቸዉ የወራሽነት ማስረጃ ጸንቶ የሚቀጥልበት የሕግ አግባብ የለም፡፡

በአጠቃላይ ተጠሪ የሟች አስር አለቃ ሀብታሙ ካሳ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ናቸዉ በማለት የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የወራሽነት ማስረጃ ለተጠሪ ሊሰጣቸዉ የሚችለዉና የሰጠዉም ማስረጃ ጸንቶ ሊቀጥል የሚችለዉ ተጠሪ በሕግ በታወቀ ግንኙነት ዉስጥ እንደተረገዙ ወይም እንደተወለዱ በማስረዳት በሕግ ግምት ልጅ መሆናቸዉን ሲረጋገጥ፤ እንዲሁም ተጠሪ ሟች ልጅነታቸዉን በማመን እንደተቀበሏቸዉ ሲያስረዱ፤ እና ተጠሪ በቤተሰብ ሕጉ መሠረት ሟች አባታቸዉ እንደሆኑ በፍርድ ቤት ዉሳኔ እንዳሰጡ ለፍርድ ቤቱ ሲያስረዱ ነዉ፡፡ተጠሪ በዚህ መልኩ ባላስረዱበት ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከቱት ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአመልካቾች ክስ የማቅረብ መብት በይርጋ የታገደ ነዉ፤ እንዲሁም አመልካቾች የመካድ ክስ እንዲያቀርቡ ሊፈቀድላቸዉ አይገባም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ በመሻር የሰጡት ዉሳኔ ሕግንና አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ያልተከተለ በመሆኑ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ለ እና ሸ) እና 10(1/ለ) መሠረት ሊታረም የሚገባዉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ ብለናል፡፡ በመሆኑም የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ የሟች ልጅ አይደሉም ሲል የሰጠዉን ዉሳኔ ከዉጤት አንጻር በማየት ሊጸና ይገባል በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ዉሳኔ</u>**

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 296421 ላይ በቀን 06/04/2015 ዓ/ም የሰጠዉ የፍርድ ዉሳኔ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 240136 ላይ በቀን 24/08/2015 ዓ.ም የሰጠዉ ትእዛዝ በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 300439 ላይ በቀን 23/12/2014ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 መሠረት ጸንቷል፡፡
3. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት በነበረዉ ክርክር ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**<u>ትእዛዝ</u>**

1. የስር ፍርድ ቤት መዝገብ ይመለስ፡፡
2. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡ሲጠይቁ ግልባጩ ለግራ ቀኙ ይሰጣቸዉ፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

3. መዝገቡ ተዝግቷል ፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ም

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሠ/መ/ቁጥር 249062

ጥቅምት 06 ቀን 2017 ዓ/ም

ዳኞች ፡- ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ብርሃኑ መንግሥቱ

ማርታ ተካ

አመልካች ፡- የቦሌ ክፍለ ከተማ መሬት ልማት ጽ/ቤት

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ ብርቅነሽ ወ/ሚካዔል

2. ወ/ሮ ፀሐይ ደምሴ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ጉዳዩ የክርክር አመራር የሚመለከት ነዉ፡፡ ክርክሩ የተጀመረዉ የአሁን 1ኛ ተጠሪ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአሁን 2ኛ ተጠሪ ላይ በመሰረቱት ክስ ሲሆን የክሱ ይዘት በአጭሩ በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 17 ቀበሌ 24 ክልል ዉስጥ መንግሥት ቦታ መርቶልኝ በቁጥር 2179 የተመዘገበ ካርታ ተሰርቶልኝ ቦታዉን ከተረከብኩ በኋላ አንድ ክፍል ቤት ሰርቼ በዘበኛ እያስጠበቅሁት እያለ ባጋጠመኝ ህመም ምክንያት በቦታዉ መኖር አልቻልኩም፡፡ዘበኛዉም በጊዜዉ በቦታዉ አለመገኘቱን አጋጣሚ ተጠቅመዉ 2ኛ ተጠሪ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የግቢዉን አጥር ከራሳቸዉ አጥር ጋር በመቀላለቀል ቤቱን ያለአግባብ ይዘዉት ይገኛሉ፡፡ ስለሆነም አለአግባብ የያዙትን ይዞታ ከነቤቱ እንዲያስረክቡኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

2ኛ ተጠሪ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማስቀደም በሰጡት መልስ በቀድሞ አጠራር ከፍተኛ 17 ቀበሌ 24 በአሁኑ ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08/09 የቤት ቁጥር 326/ሠ የሆነ በ1470 ካሬ ሜትር ላይ የሚገኝ 2ኛ ተጠሪ የምኖርበትን ቤት በቀን 28/12/1982 ዓ/ም በተጻፈ የመኖሪያ ቤት ሽያጭ ዉል ከሻምበል ሽባባዉ ዋለልኝ እና ከወ/ሮ ሐረገወይን መርዕድ የገዛሁት ነዉ፡፡በስሜ ግብር እየገበርኩበት ይዤ የምገኘዉ ይዞታ ስለሆነ ክሱ ዉድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 186581 ላይ ግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃዎችን እንዲሁም አከራካሪዉን የመሬት ይዞታ ከሚያስተዳድረዉ አካል ያስቀረበዉን ማስረጃ መርምሮ በቀን 24/03/2006ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ የ2ኛ ተጠሪ ይዞታ በማህደር 429 ካሬ ሜትር እንደሆነና 936 ካሬ ሜትር ትርፍ ይዘዉት እንደሚገኙ፤ይህን ትርፍ ቦታ ይካተትልኝ ብለዉ አመልክተዉ እንደነበረና በምን ምክንያት እንዳልተካተተ የሚያዉቁት ነገር እንደሌለ፤የ1ኛ ተጠሪ ይዞታ 1500 ካሬ ሜትር ለዶሮ እርባታ ተብሎ የተሰጣቸዉ መሆኑና የወንዝ መዳረሻ መሆኑ፤2ኛ ተጠሪ በጠቅላላ የያዙት የቦታ ስፋት 1461 ሜትር ካሬ መሆኑ ቀበሌዉ የተለያየበት ምክንያት በወቅቱ ቀበሌ 17/21 ተብሎ ይጠራ እንደነበረ በአሁኑ ቀበሌ 17/24 ተብሎ እንደሚጠራ በማብራራት መልስ ልኳል፡፡2ኛተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆነ ይዞታ ትርፉን ለረዥም ጊዜ አጥሬ ስለያዝኩት የራሴ ነዉ ከሚል በቀር በመንግሥት የተሰጣቸዉ መሆኑ የሚያስረዳ ማስረጃ አላቀረቡም፡፡2ኛ ተጠሪ ከራሳቸዉ ይዞታ ዉጭ ያለ ቦታ ለዶሮ እርባታ እንደተሰጣቸዉ ፍርድ ቤቱ በክፍለ ከተማዉ የሚገኘዉን 1ኛ ተጠሪ ማህደር አስቀርቦ አረጋግጧል፡፡በዚህ መሠረት 1ኛ ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆነ ይዞታ የራሳቸዉ መሆኑ የማያስረዳ የባለህብተነት ምስክር ወረቀት የያዙበት ስለሆነና 2ኛ ተጠሪም ከይዞታቸዉ ዉጭ ያለ ትርፍ ቦታ የራሳቸዉ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ ስላላቀረቡ 2ኛ ተጠሪ ትርፍ የያዙትን 1032 ካሬ ሜትር ለ1ኛ ተጠሪ ለቀዉ ሊያስረክቡ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

ከዚህ ቀጥሎ 2ኛ ተጠሪ በቀን 17/02/2007ዓ/ም በተጻፈ አቤቱታ የአሁን 1ኛ ተጠሪ በይዞታዉ ላይ አጥርም ሆነ ቤት ሳይሰሩ በሐሰት በተንኮል በወንጀል ጠቀስ ተግባር ዉሳኔ ያሰጡ በመሆኑና ካርታዉም ስለመከነ የተሰጠዉ ዉሳኔ በዳግም ዳኝነት ታይቶ የሻርልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡ የአሁን 1ኛ ተጠሪ በሰጡት መልስ የ2ኛ ተጠሪ አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 6 ላይ የተደነገጉትን መስፈርቶች ስለማያሟላ ዳግም ዳኝነት ይታይልኝ በማለት ያቀረቡ አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤትም 2ኛ ተጠሪ ያቀረቡትን ዳግም ዳኝነት ይታይልኝ አቤቱታ መርምሮ 2ኛ ተጠሪ መክነ ያሉት ካርታ ወደ ነበረበት እንዲመለስ የተወሰነ እና ቀድሞውንም መክነ የተባለው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 6(1/ሀ) ስር በተዘረዘሩት ምክንያቶች ባለመሆኑ 2ኛ ተጠሪ ባቀረቡት የዳግም ዳኝነት አቤቱታ ጥያቄ ሊታይ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የሚገባው አይደለም በማለት በቀን 19/10/2007ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ ውድቅ አድርጎታል፡፡በዚህ ዉሰኔ ቅር በመሰኘት 2ኛ ተጠሪ ለዚህ ሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርበዉ በመ/ቁጥር 116118 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 27/03/2009ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ 2ኛ ተጠሪ ያቀረቡትን አቤቱታ መርምሮ 2ኛ ተጠሪ ያቀረቡት የዳግም ዳኝነት ይታይልኝ ጥያቄ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 6(1 እና 2) የተደነገጉትን መስፈርቶች የሚያሟላ በመሆኑ ዳግመኛ ዳኝነት ሊታይ ይገባል በማለት የስር ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የሰጠዉን ዉሳኔ በመሻር መልሷል፡፡

ይህ ሰበር ችሎት ከላይ በተገለጸዉ መሠረት በመ/ቁጥር 116118 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 27/03/2009ዓ/ም ዉሳኔ ከመስጠቱ በፊት የአሁን አመልካች በቀን 22/11/2007ዓ/ም በተጻፈ አቤቱታ በስር ፍርድ ቤት በሰ/መ/ቁጥር 186581 ላይ በቀን 19/10/2007ዓ/ም በዋለዉ ችሎት 2ኛ ተጠሪ ከይዞታዉ ዉጭ አጥረዉ የያዙትን 1032 ካሬ ሜትር ይዞታ ለ1ኛ ተጠሪ ለቀዉ ያስረክቡ ሲል የሰጠዉ ዉሳኔ ይዞታዉ የመንግሥት ስለሆነ መብቴን ይነካል በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 የፍርድ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ለዚህ አቤቱታ ተጠሪዎች በተናጠል በቀን 29/02/2008ዓ/ም የተጻፈ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያለበትን መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡በዚህ መልኩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 መሰረት በቀረበ አቤቱታ ላይ ክርክር ከተሰማና በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት በተነሳ መከራከሪያ ላይ ብይን ተሰጥቶ ዉድቅ ከተደረገ በኂላ በዚህ መልኩ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 186581 ላይ እየታየ ያለዉ ክርክር የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 116118 ላይ ዉሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 197 መሠረት ታግዶ እንዲቆይ የአሁን 2ኛ ተጠሪ አመልክተዋል፡፡ፍርድ ቤቱም ማመልከቻዉን ተቀብሎ በቀን 03/09/2008ዓ/ም በዋለዉ ችሎት መዝገቡ ተዝግቶ እንዲቆይ ማዘዙን ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡

ከላይ በተመለከተዉ መሠረት አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 መሰረት አቤቱታ ባቀረበዉ አቤቱታ መነሻ የተደረገዉ ክርክር ከላይ የተገለጸዉ ደረጃ ደርሶ በጊዜያዊነት ከታገደ በኂላ የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በቀን 01/10/2009ዓ/ም በዋለዉ ችሎት በሰጠዉ ትእዛዝ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁጥር 116118 ላይ በቀን 27/03/2009ዓ/ም ዉሳኔ መስጠቱንና ዉሳኔዉም 2ኛ ተጠሪ ያቀረቡት የዳግም ዳኝነት አቤቱታ ታይቶ እንዲወሰን ጉዳዩ እንደተመለሰለት የሚገልጽ እንደሆነ በመዝገቡ ላይ በማስፈር የአሁን አመልካች ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉን ዉሳኔ ግልባጭ በመዉሰድ በክርክሩ ተካፋይ እንዲሆን በሚፈቅድለት የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ መሰረት ወደ ክርክሩ ሊያስገባዉ የሚችለዉን መልስ እንዲሰጥ በማለት አዝዟል፡፡ ይህንን ትእዛዝ ተከትሎ የአሁን አመልካች የሕዝብና የመንግሥት የሆነን ይዞታ የመቆጣጠርና የመከላከል መብት አለኝ በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 41 መሰረት በክርክሩ ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር እንዲፈቀድለት በቀን 26/10/2009ዓ/ም የተጻፈ አቤቱታ ማቅረቡን እና ተጠሪዎችም በዚህ አቤቱታ ላይ ያላቸዉን ክርክር ካሰሙ በኂላ ፍርድ ቤቱ በቀን 23/02/2010ዓ/ም በዋለዉ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ችሎት በሰጠዉ ብይን የአሁን አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 41 መሰረት በክርክሩ ተካፋይ እንዲሆን መወሰኑን ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡

በመቀጠልም ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር እና የቀረቡለትን ማስረጃዎች መርምሮ በቀን 20/11/2012 ዓ/ም በሰጠዉ የፍርድ ዉሳኔ 2ኛ ተጠሪ ስፋቱ 429 ካሬ ሜትር የሆነ ይዞታ በግዢ እንዳገኙት እና ለዚሁ ይዞታም የይዞታ ማረጋገጫ እንዳላቸው ከቀረቡት ማስረጃዎች መረዳት ተችሏል፡፡ 936 ካሬ ሜትር የሆነውን እና አስፋፍተው የያዙት ትርፍ ይዞታም ተካቶ መረጃ እንዲሰጣቸው ጠይቀው ቅጽ ተሞልቶላቸዋል፡፡ 1470 ካሬ ሜትር ለሆነ ይዞታም ከ1992 ዓ.ም ጀምሮ የቦታ ግብር ሲገብሩ ቆይተዋል፡፡ ስለሆነም 2ኛ ተጠሪ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1168/1 መሠረት ባለይዞታ መሆናቸው ግምት ይወሰዳል፡፡ የ1ኛ ተጠሪ ካርታ ቁጥር 2179 በ1970 ዓ.ም ሲሰጥ በካርታው ላይ እንደተገለጸው ቦታው የሚጸናው በስድስት ወራት ውስጥ ቤት ሲሰራበት ነው፡፡ ሆኖም አመልካች ለ34 ዓመታት ቤት ስላልሰሩበት በመመሪያ ቁጥር 12/2004 አንቀጽ 16 መሠረት ካርታው መክኗል፡፡ ከመመሪያው ውጪ እንደገና ካርታው እንዲጸና የተደረገው ሙከራ ሕገ-ወጥ መሆኑ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማት እና ማኔጅመንት ቢሮ በቀን 03/09/2007 ዓ.ም በተጻፈ ሸኚ ደብዳቤ በአሰራር ጥራት ኦዲት ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ጽ/ቤት በቀን 17/10/2011 ዓ.ም የ1ኛ ተጠሪ ካርታ መክኗል ለማለት አይችልም በማለት ምላሽ ቢሰጥም በመዋቅር ደረጃ የበላዩ የሆነው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማት ማኔጅመንት ቢሮ የተቃረነ ምላሽ ሰጥቷል፡፡ ይህም ቢታለፍ ካርታው የመከነው 1ኛ ተጠሪ በካርታው ላይ የተገለጸውን በስድስት ወራት ውስጥ ቤት የመስራት ግዴታ ባለመወጣታቸው ነው፡፡ ስለሆነም ፍርድ ቤቱ አመልካች መስሪያ ቤት በቀን 17/10/2011 ዓ.ም የሰጠውን ምላሽ አልተቀበለውም፡፡ በግብር ሰነዶች ላይ 1470 ካሬ ሜትር በሚል የተጠቀሰው 1461 ካሬ ሜትር ይዞታ የ2ኛ ተጠሪ ይዞታ በመሆኑ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጲያ አርክቴክቸር የህንጻ ግንባታ እና ከተማ ልማት ኢንስቲትዩት ለፍርድ ቤቱ በቀን 22/04/2012 ዓ.ም በሰጠው ምላሽ የ1ኛ ተጠሪ እና የ2ኛ ተጠሪ ይዞታ ኩታገጠም መሆኑን የሚያመለክት መሆኑ ተገናዝቦ በትርፍነት ግራ ቀኙን የሚያከራክረው 1032 ካሬ ሜትር ይዞታ የ2ኛ ተጠሪ በመሆኑ ለ1ኛ ተጠሪ ሊያስረክቡ አይገባም በማለት ቀደም ሲል በመዝገቡ በቀን 24/03/2006 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረውን ፍርድ ሽሮታል፡፡

ከላይ በተገለጸዉ መሠረት በተሰጠ ዉሳኔ የአሁን 1ኛ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 259329 ላይ ባቀረቡት ይግባኝ አከራካሪዉ ይዞታ የ2ኛ ተጠሪ መሆኑን የሚያስረዳ የተሻለ ማስረጃ ያላቸዉ 2ኛ ተጠሪ ናቸዉ መባሉ አግባብ አይደለም በማለት እንዲሻርላቸዉ፤ የአሁን አመልካች ደግሞ በመ//ቁጥር 259790 ላይ ባቀረበዉ ይግባኝ የስር ፍርድ ቤት ባቀረብነው የጣልቃገብነት አቤቱታ ላይ ምንም ሳይል በዝምታ ውሳኔ መስጠቱ ተገቢ አይደለም መሬቱ የግራ ቀኙ ሳይሆን የመንግስት ነው በማለት ያነሳነው ክርክር መታለፉም አግባብ አይደለም በማለት ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ አቤቱታዎች አቅርበዉ ፍርድ ቤቱም ሁለቱንም መዝገቦች አጣምሮ ግራ ቀኙን በመ/ቁጥር

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

259329 ላይ አከራክሮ በቀን 30/10/2013 ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ የአሁን ሁለቱም ተጠሪዎች ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ይዞታ ላይ መብት ያላቸው ስለመሆኑ ያቀረቡት ማስረጃ ማረጋገጥ ባለመቻላቸው እና ማንኛውም በግለሰቦች ያልተያዘ የከተማ ቦታ የመንግስት እና የሕዝብ መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 47/67 በተደነገገው መሰረት ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ይዞታ የመንግስት ነው በማለት የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡

ከዚህ በመቀጠል የአሁን 1ኛ ተጠሪ የሰበር አቤቱታቸዉን በመ/ቁጥር 213741 ላይ አቅርበዉ ይህ ችሎትም ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 04/02/2015ዓ/ም በአብላጫ ድምጽ በሰጠዉ የፍርድ ዉሳኔ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ 1032 ካሬ ሜትር ይዞታ ሕጋዊ ባለይዞታ የአሁን 1ኛ ተጠሪ እንደሆኑ ተገልጾ የተሰጣቸው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በሙስና የተሰጠ ሊሆን ይችላል በሚል ጥርጣሬ የጸረ ሙስና ኮሚሽን የወንጀል ምርመራ እያካሄደባቸው ነው በሚል የቀረበ መከራከሪያ ቢኖርም አመልካች የተሰጣቸው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በሙስና የተሰጠ ነው በማለት ተረጋግጦ የተሰጠ ውሳኔ ስለመኖሩ የሚያመለክት ክርክርም ሆነ ማስረጃ አልቀረበም፡፡1ኛ ተጠሪ ጉዳዩን ለማስወሰን በሐሰት ተዘጋጅቶ የቀረበ ሠነድ ወይም ሐሰተኛ የምስክርነት ቃልን ወይም መደለያን ወይም ወንጀል ጠቀስ የሆነ ተግባርን መሠረት በማድረግ ያሰጡት ውሳኔ ያለ ስለመሆኑ የሚያመላክት ማስረጃ አልቀረበም፡፡ ስለሆነም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአመልካች እና በ2ኛ ተጠሪ መካከል በተደረገው ክርክር በቀን 24/03/2006 ዓ.ም ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ አስተዳደሩ የወሰደውን እርምጃ መሰረት በማድረግ 2ኛ ተጠሪ ባቀረቡት የዳግም ዳኝነት አቤቱታ መነሻነት የአሁን አመልካች ጣልቃ እንዲገባ አድርጎ አስቀድሞ የተሰጠውን ውሳኔ መሻሩ፤ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ይህንኑ ማረም ሲገባው ይዞታው የመንግስት ነው በማለት መወሰኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡ በመሆኑም በተጠሪዎች መካከል በተደረገው ክርከር መነሻነት በቀን 24/03/2006 ዓ.ም የተሰጠው ፍርድ ሊሻር አይገባም በማለት ወስኗል፡፡

በመቀጠል የአሁን አመልካች በቀን 19/05/2015 ዓ/ም በተጻፈ አቤቱታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በጉዳዩ ላይ በመ/ቁጥር 213741 ላይ የመጨረሻ ዉሳኔ ስለሰጠ በመዝገቡ ላይ በቀን 03/09/2008ዓ/ም በዋለዉ ችሎት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 197 መሠረት የተሰጠዉ እግድ ተነስቶ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 መሠረት ያቀረብኩት አቤቱታ ተሰምቶ ይወሰንልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ታግዶ እንዲቆይ የአሁን 2ኛ ተጠሪ አመልክተዋል፡፡ፍርድ ቤቱም ማመልከቻዉን ተቀብሎ የተጠሪዎችን አስተያየት ሰምቶ በቀን 06/06/2015 ዓ/ም እና 22/06/2015ዓ/ም በዋለዉ ችሎት በሰጠዉ ትእዛዝ አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 መሰረት ያቀረብኩት አቤቱታ ይሰማልኝ በማለት አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም ራሱ በክርክሩ ተካፋይ በመሆን ተከራክሮ የተሰጠዉ ዉሳኔ እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ታይቶ በተሰጠ የመጨረሻ ዉሳኔ ስለጸና አቤቱታዉ መዝገቡን ማንቀሳቀስ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358ን ዓላማ የተከተለ አይደለም በማለት ዉድቅ አድርጓል፡፡ አመልካች በዚህ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 305704 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 29/09/2015ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን አቤቱታ ዉድቅ ማድረጉ በአግባቡ ነዉ ሲል አጽንቷል፡፡

አመልካች በቀን 13/10/2015 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉ ከላይ በተመለከተዉ መሠረት በተሰጠ ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱ በአጭሩ - የመንግስት በሆነዉና በማንም ያልተያዘ ይዞታ ላይ በተሰጠዉ ዉሳኔ ላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 መሰረት ላቀረብነዉ አቤቱታና ዳኝነት ምንም ሳይባል ወይም በመተዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 6 መሰረት ዳግም ዳኝነት በተጠየቀበት ጉዳይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 41 መሰረት አመልካች ወደ ክርክሩ እንዲገባ መወሰኑ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉን ዓላማ እና የአመልካችን ፍትህ የማግኘት መብት የጣሰ ስህተት ነዉ፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 መሰረት ያቀረብነውን የመቃወም አቤቱታ በመ/ቁጥር 186581 ላይ በቀን 03/09/2008 ዓ/ም በተሰጠ ትእዛዝ የማንቀሳቀስ መብታችንን ጠብቆ በተዘጋው መሰረት መዝገቡን እንዲያንቀሳቅስልን አቤቱታ ብናቀርብም የስር ፍርድ ቤቶች አቤቱታችንን ውድቅ ማድረጋቸዉ የአመልካችን መሠረታዊ መብት የጣሰ ነዉ፡፡ስለሆነም በክርክር አመራር ጉድለት ምክንያት አመልካች መሠረታዊ መብት ሊጣስ ስለማይገባ አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 6 መሰረት በሚታይ የዳግም ዳኝነት ክርክር ጣልቃ እንዲገባ መደረጉ ስህተት ነዉ ተብሎ ተሽሮ አመልካች የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 መሠረት ያቀረብኩት አቤቱታ ተመርምሮ እንዲወሰን ጉዳዩ ለስር ፍርድ ቤት እንዲመለስ ይወሰንልን በማለት አመልክቷል፡፡

ችሎቱ የሰበር አቤቱታዉን ከስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ጋር አገናዝቦ መርምሮ አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ ሕግ ቁጥር 358 መሰረት ባቀረበዉ የመቃወም ማመልከቻ ላይ የመጨረሻ ዉሳኔ ሳይሰጥበት መታለፉ ሕጋዊ መሆን አለመሆኑ? የመቃወም ማመልከቻ በቀረበበት ጉዳይ ዳግም ዳኝነት ከቀረበ መጀመሪያ መስተናገድ ያለበት የትኛው ክርክር ነው፣ አመልካች በዳግም ዳኝነት ክርክሩ ላይ በጣልቃ-ገብነት መሳተፉ የመቃወም ማመልከቻ መሠረት አድርጎ ያቀረበውን ክርክር እንደተወ ያስቆጥራልን፣ በሰበር ሰሚ ችሎቱ በመቃወም ማመልከቻ ላይ የተሰጠ ውሳኔ በሌለበት ጉዳዩ የመጨረሻ ውሳኔ በሰበር ሰሚ ችሎት ተሰጥቶበታል መባሉ ሕጋዊ መሆን አለመሆኑ፣ አመልካች ተቃውሞ ያቀረበዉ በሥር ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ በተሰጠው ፍርድ ላይ ከመሆኑ አኳያ አቤቱታውን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተመልክቶ ባለመወሰኑ ከክርክር አመራር ሥርዓት አንጻር መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑ? እንዲመረመር ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ አዝዟል፡፡

1ኛ ተጠሪ በቀን 10/03/2016ዓ/ም ጽፈዉ ያቀረቡት መልስ ይዘት በአጭሩ - የአሁን አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 መሠረት ያቀረበዉን መቃወሚያ ትቶ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 41 መሰረት አቤቱታ በማቅረብ ጣልቃ ገብቶ በተከራከረበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 መሰረት ያቀረብኩት አቤቱታ

አልታየልኝም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 41 መሰረት ጣልቃ እንዲገባ መደረጉም ስህተት ነዉ በማለት ያቀረበዉ አቤቱታ ሀሰት ነዉ፡፡እንዲሁም አመልካቹ አቤቱታዬ በአግባቡ ተመርምሮ አልተወሰነም የሚለዉን ጨምሮ ታለፈብኝ የሚለዉን መብትና ማናቸዉንም በስር ፍ/ቤቱ ተፈጸሙ የሚላቸዉን መሠረታዊና የሥ/ሥርዓት ግድፈቶች በማካተት በቀን 11/01/2013 ዓ.ም የተጻፈ ይግባኝ አቅርቦ ይግባኙ በመ/ቁጥሩ 259790 ላይ ሲታይ ከቆየ በኋላ ይህ መዝገብ እኔ ይግባኝ ካቀረብኩበት መ/ቁጥር 259329 ጋር ተጣምሮ ታይቶ በቀን 30/10/2013 ዓ.ም ዉሳኔ አግኝቷል፡፡ሆኖም ይህ ዉሳኔ በመጨረሻ በሰበር ሰሚ ችሎቱት በሰ/መ/ቁጥር 213741 ላይ በቀን 4/02/2015 ዓ.ም በተሰጠ ዉሳኔ ተሽሯል፡፡ጉዳዩ በዚህ አግባብ ታይቶ የመጨረሻ ዉሳኔ ካገኘ ከ3 ዓመት በኋላ አመልካች ይህንን አቤቱታ ሊያቀረብ የሚችልበት አንዳች ሕጋዊም ሆነ ሥነ ሥርዓታዊ ምክንያት የለም፡፡አመልካች በራሱ ጉድለት ያጣዉ መብት ቢኖር እንኳን በሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 212 እና በሰ/መ/ቁጥር 67127 ላይ በተሰጠዉ የሕግ ትርጉም መሰረት ተቀባይነት የለዉም፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ከተደነገገበት ዓላማዎች መካከል አንድ ሰዉ ይመለከተኛል በሚለዉ ጉዳይ ክርክሩ እንዳለበት ደረጃ በጣልቃ ገብነት ወይም በተቃዋሚነት የክርክሩ ተካፋይ ባለመሆኑ መብቱ እንዳይጎዳ መከላከል በአንጻሩ አንድ ተከራካሪ ወገን በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ ክስ ወይም ተመሳሳይ ክርክር እያቀረበ የሌላዉን ወገንም ሆነ የፍርድ ቤትን ጊዜ እንዳያባክንና ለተጨማሪ ወጪ እንዳይዳርግ ማድረግ በመሆኑ አመልካች ከዉሳኔ በፊት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 41 መሠረት ቢገባም ሆነ ከዉሳኔ በኋላ በቁጥር 358 መሠረት ቢገባ ዋናዉ ነገር ክርክሩን አዉቆት የክርክሩ ተካፋይ መሆኑ በመሆኑ አመልካችም ክርክሩ መኖሩን አዉቆ በክርክሩ ጣልቃ ገብቶ መከራከሩ ተረጋግጦ ቀጥሎ ፍርዱን በመቃወም ያቀረብኩት አቤቱታ ይታይልኝ በማለት ያቀረበዉ አቤቱታ ዉድቅ የተደረገበት አግባብ ይህንን ዓላማ በሚያሳካ መልኩ በስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ መሰጠቱን የሚያሳይ በመሆኑ አመልካች የሥነ ሥርዓት ሕጉን ዓላማ የሚቃረን ነዉ ማለቱ ተቀባይነት የለዉም፡፡ አመልካቹ በ22/11/2007 ዓ.ም እና በ26/10/2009 ዓ.ም ባቀረባቸዉ አቤቱታዎች መነሻነት ከመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እስከ ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ በክርክሩ ተካፋይ ሆኖ በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ዉሳኔ ስለተሰጠ እና የክርክሩን ዉጤት ጠብቆ ስለቀረበ በሰ/መ/ቁጥር 181236 እና 56795 ላይ በተሰጠዉ የሕግ ትርጉም መሰረት አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 መሠረት ያቀረበዉ አቤቱታ የሚታይበት ሥነ ሥርዓታዊ አግባብ የለም፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 መሰረት ያቀረብኩት መቃወሚያ ይታይልኝ በማለት ያቀረበዉን አቤቱታ ዉድቅ በማድረጋቸዉ የተፈጸመ ስህተት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

2ኛ ተጠሪ በቀን 30/01/2016ዓ/ም በተጻፈ መልሳቸዉ - አከራካሪ ለሆነው 1032 ካሬ ሜትር ቦታ ኩታ ገጠም የሆነ 429 ካሬ ሜትር ላይ የረፈ መኖሪያ ቤት ከ1970 ዓ.ም በፊት በመንደር ውል ገዝቼ ከቀን 28/12/1982 ዓ.ም ጀምሮ ግን ይህ የመንደር ውል ወደ ሕጋዊ ውል ተቀይሮ የግዢ ስመ-ሀብቱ በሕጋዊ መንገድ ወደ እኔ ዞሮ 429 ካሬ ሜትር ላይ የረፈውን መኖሪያ ቤት ይዤ ስቆይ ይህ አከራካሪው 1032 ካሬ

ሜትር የሆነው መሬት ወንዝ ዳር በመሆኑ በውሃ የተበላ እና ዙሪያውን በጫካ የተዋጠ ስለሆነና ባለቤት አልባ እና የአካባቢው ቆሻሻ መጣያ መሬት በመሆኑ በእጄ ካለው 429 ካሬ ሜይዞታ ላይ ተካቶ እንዲሠጠኝ እና ከኔው ይዞታ ጋር አጥሬበት እንዳለማው ለቦሌ ክፍለ ከተማ ለወረዳ 5 መሬት አስተዳደር እና ግንባታ ፈቃድ ጽ/ቤት አመልክቼ ጽ/ቤቱም ይህ መሬት ጠፍ እና ደናማ ሆኖ በማንም ያልተያዘ መሆኑን የመሬት አስተዳደር እና ግንባታ ፈቃድ ጽ/ቤቱ አረጋግጦ በካዳስተርም የራሱ የሆነ መለያ ቁጥር ተሠጥቶት በወቅቱ የሚሞላውን ቅጽ በራሴ በ2ኛዋ መልስ ሰጪ ስም አስሞልቶ አንድ ላይ ደምሮ 1461 ካ/ሜትር ሰጥቶኝ ከ1992 ዓ.ም ጀምሮ እስካሁን ድረስ እየገበርኩበት ብዙ ቤቶችንም ሠርቼበት በውስጡ እየኖርኩ ፣ ቋሚ ዛፎችን እና አትክልቶችን በመትከል ከብር 5,000,000 በላይ ወጪ በማድረግ ያለማሁትና የያዝኩት ይዞታ ነዉ። ስለሆነም አመልካች ባቀረበዉ አቤቱታ መሰረት የተፈጸመዉ ሥነ ሥርዓታዊ ስህተት ታርሞ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ይዞታ የ2ኛ ተጠሪ ነዉ ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት ተከራክረዋል። አመልካች በ2ኛ ተጠሪ መልስ ላይ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክሯል።

ከላይ አጠር ባለ መልኩ የተገለጸዉ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠ ዉሳኔ እንዲሁም ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት ያቀረቡትን ክርክር የሚመለከት ሲሆን እኛም አስቀድሞ የተያዘዉን ጭብጥ መሰረት በማድረግ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የሕግ ስህተት መፈጸም አለመፈጸሙን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል።

እንደተመረመረዉም በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40/1 በንብረት ሕግ እና በሌሎች ሕግጋት ላይ እንደተመለከተዉ ማንኛውም ሰዉ በንብረት መብቱ ላይ ጥሰት እንዳይፈጠርበት በሕግ ጥበቃ ተደርጎለታል። እንዲሁም በዚሁ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40/6 ስር የመሬት ባለቤትነት የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ መንግሥት የግለሰቦችን የመጠቀም መብት እንደሚያስከብር ተደንግጓል። በዚህ አግባብ ለመብቱ ጥበቃ ከመደረጉም በተጨማሪ በማንኛውም ሰዉ የንብረት መብት ላይ ጥሰት እንዳይፈጠር እና ተጥሶ ሲገኝም የተጣሰዉን መብት ማስከበር የሚቻልበት ሥርዓት በሕገ መንግሥቱና በየተዋረዱ ባሉ ሕግጋት ተዘርግቷል።በዚህ መሠረት የንብረት መብቴ ተጥሶብኛል የሚል ማንኛዉም ሰዉ የንብረት ይዞታ ወይም የመሬት ይዞታ ባለይዞታነት መብት (holding right) ይገባኛል ወይም በዚህ መብት እንዳልጠቀም የተፈጸመዉ ሕገ-ወጥ ተግበር ይወገድልኝ በማለት በሚያቀርበዉ ክስ (The Possessory Action) ወይም የንብረት ባለቤትነትን በመፋለም በሚያቀርበዉ ክስ (The Petitory Action) ለማስከበር ዳኝነት ሊጠየቅ ይችላል።

እንዲሁም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 41 ስር እንደተደነገገዉ ሌሎች ተከራካሪዎች በሚከራከሩበት ጉዳይ ያገባኛል የሚል ሦስተኛ ወገን ከፍርድ ዉሳኔ በፊት ጣልቃ ገብ ሆኖ ለመከራከር ይችላል።በዚህ መልኩ በሌሎች ሰዎች መካከል በሚደረገዉ ክርክር ጣልቃ በመግባት የክርክሩ ተካፋይ ለመሆን የሚፈልግ ሦስተኛ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ወገን ለክርክሩ መነሻ በሆነዉ ሀብት ወይም ነገር ላይ ስላለዉ መብት እና/ወይም ጥቅም እና በክርክሩ ላይ በሚሰጠዉ ዉሳኔ በቀጥታ መብቱ እና/ወይም ጥቅሙ የሚነካበት መሆኑን በጣልቃ ገብነቱ ማመልከቻ ላይ በዝርዝር ማሳየት ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም ጣልቃ ለመግባት ማመልከቻ የሚያቀርበዉ ሰዉ (1) ክርክር እየተደረገ ባለበት ነገር(ሀብት) በሕግ ጥበቃ ሊደረግለት የሚገባ መብት/ጥቅም ያለዉ መሆኑን ማረጋገጥ፣(2) መብቱ/ጥቅሙ በፍርድ ሊረጋገጥ የሚችል መሆኑን ማረጋገጥ እና (3) ጥያቄዉንም ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት ማቅረብ እና በፍርድ ቤቱ ሲፈቀድለት በክርክሩ ሦስተኛ ወገን ተከራካሪ ሆኖ ተካፋይ ሊሆን ይችላል፡፡

በሌላ በኩል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 ስር እንደተደነገገዉ በክርክሩ ዉስጥ ተካፋይ መሆን የሚገባዉ ወይም በክርክሩ ዉስጥ ለመግባት የሚችል ሆኖ ነገር ግን በክርክሩ ተካፋይ ሳይሆን መብቱን የሚነካ ዉሳኔ የተሰጠበት ማንኛዉም ሰዉ መብቱን የሚነካበት ፍርድ ከመፈጸሙ በፊት ፍርዱን በመቃወም አቤቱታ ማቅረብ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ በዚህ አግባብ የተደነገገበት ምክንያት ከፍርድ በኋላም ቢሆን በክርክሩ ተከፋይ መሆን የሚገባቸዉና በተሰጠዉ የፍርድ ዉሳኔ መብታቸዉ የተነካባቸዉ ሰዎች ፍርዱን በዚያዉ መዝገብ ላይ ተቃዉመዉ በክርክሩ ተሳታፊ የሚሆኑበትንና መብታቸዉን ሊያስከብሩ የሚችሉበትን ስርዓት በመዘርጋት ክርክሮች በተቻለ መጠን በአንድ መዝገብ ላይ ተሰምተዉ ወጥነት ያለዉን እና ሊፈጸም የሚችል ዉሳኔ መስጠት እንዲቻል ነዉ፡፡ በዚህ ድንጋጌ በግልጽ እንደተመለከተዉ ፍርድን በመቃወም የሚቀርብ አቤቱታ መቅረብ የሚገባዉ መቼ ነዉ የሚለዉን ለመመለስ ሕጉ ተቃዉሞ የቀረበበት ፍርድ ከመፈጸሙ በፊት የሚል መስፈርት በማስቀመት ደንግጓል፡፡ ይህም ፍርድን በመቃወም የሚቀርብ አቤቱታ በማንኛዉም ጊዜ የሚቀርብ እንዳልሆነ የሚያስገነዝብ ነዉ፡፡ እንዲሁም መቃወሚያ በማን መቅረብ አለበት የሚለዉን በተመለከተ በክርክሩ ተካፋይ ባልሆነና በተሰጠዉ ፍርድ መብቱ በተነካበት ሰዉ መሆን እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ በዚህ አግባብ ፍርድን በመቃወም የሚቀርብ አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ከቁጥር 358-360 ስር ከተደነገገዉ አንጻር ይመራል፡፡

ከላይ በተመለከተዉ አግባብ ከሚቀርበዉ ክርክር ሌላ በልዩ ሁኔታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 6 ስር እንደተደነገገዉ በዉስን ምክንያት አንድ ጉዳይ የመጨረሻ ዉሳኔ ካገኘ በኋላ ዳግመኛ ዳኝነት የሚታይበት ሥነ ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡ ዳግመኛ ዳኝነት የሚታይበት ሥነ ሥርዓት በመፈቀዱ ክርክሮች በየደረጃዉ ባሉ ፍርድ ቤቶች በተለያየ የክርክር ደረጃ እየታዩ የሥነ ሥርዓት ሕጉ ዓላማ ሳይሳካ እንዳይቀር ይህ ልዩ ሁኔታ በጠባቡ ተግባራዊ እንዲደረግ የሚያስችሉ ድንጋጌዎች ተደንግጓል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት ዳግመኛ ዳኝነት ሊታይ የሚችለዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 6(1 እና 2) ስር የተደነገጉ መስፈርቶች ሲሟሉ ብቻ ሲሆን የዳግመኛ ዳኝነት አቤቱታ ሊቀርብ የሚችለዉም ሆነ ይህንን አቤቱታ ተከትሎ ክርክር ሊደረግ የሚችለዉ አስቀድሞ በክርክሩ ተካፋይ በሆኑ ተከራካሪ ወገኖች መካከል ብቻ ነዉ፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ከፍ ሲል እንደተገለጸዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 6 መሰረት ዳግመኛ ዳኝነት አቤቱታ ማቅረብ የሚችሉትና በዚህ አቤቱታ መነሻ በተከራካሪነት ተካፋይ መሆን የሚችሉቱ ዳግመኛ ዳኝነት የተጠየቀበት ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት በነበረዉ ክርክር ተከራካሪ የሆኑ ወገኖች ናቸዉ፡፡በአንጻሩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 መሰረት የፍርድ መቃወሚያ ሊያቀርብ የሚችለዉ በክርክሩ ተካፋይ ባልነበረ ሦስተኛ ወገን ነዉ፡፡ከዚህ ድንጋጌ አፈጻጸም ጋር በተያያዘ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 40229 ፣ 93987 (በቅጽ 9 እና 16) እና 230658 ላይ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

ከላይ በተገለጸዉ መሠረት በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ የክርክር አመራር የተዘረጋበት ዓላማም በማስረጃ ሊረጋገጥ የሚችል የፍሬ ነገር እና በሕግ ላይ ተመስርቶ ዉሳኔ ሊሰጥበት የሚገባ ነጥብ በመለየት ለክርክሮች ምክንያታዊ በሆነ አጭር ጊዜ እና በዉስን የሰዉና የገንዘብ ሀብት ፍትሐዊ እልባት መስጠት እንዲቻል ነዉ፡፡ ክርክሮችን በሥነ ሥርዓት ሕጉ በተዘረጋዉ ሥርዓት መሰረት እየተቆጣጠሩ መምራት የፍርድ ቤቶች ኃላፊነት እንደመሆኑ ተከራካሪዎች ክርክሮቻቸዉን በቅን ልቦና እና በእዉነተኛነት መርሆዎች ላይ ተመስርተዉ የተዘረጋላቸዉን ሥነ ሥርዓታዊ መርሆዎችና ደንቦችን ተከትለዉ መከራከራቸዉን ማረጋገጥ፤ ከዚህ ዉጭ በሆነ አግባብ ክርክር እያቀረቡ የፍትሐ ብሔር ፍትህ አስተዳደሩን አለአግባብ ተጠቅመዉ ሲገኙ የማስተካከያ እርምጃ በዚሁ ሕግ መሰረት መዉሰድ ይኖርባቸዋል፡፡ተከራካሪዎችም ይህንኑ ግዴታቸዉን በአግባቡ መወጣት ይኖርባቸዋል፡፡ በአንጻሩ የፍትሐ ብሔር ጉዳይ የቀረበለት ፍርድ ቤት ክርክሮችን በተዘረጋላቸዉ ሥነ ሥርዓት መሠረት የመምራት ፣በተጠየቀዉ ዳኝነት እና በአከራከረዉ ጭብጥ ላይ ተገድቦ ዉሳኔ የመስጠት ኃላፊነቱን በአግባቡ ተግባራዊ ሳያደርግ ክርክር የሚመራ ከሆነ ክርክሩ ከጊዜ፣ከገንዘብና ከሰዉ ሀብት (judicial economy) አጠቃቀም አኳያ ዉጤታማ እንዳይሆን በማድረግ ፍትሕን በማጓደል የተከራካሪ ወገኖችን ሥነ ሥርዓታዊ ፍትሕ (procedural justice) ከማጓደል አልፎ የተከራካሪ ወገኖችን የስረ ነገር መብት(substantive right) እስከማሳጣት የሚያደርስ ጉዳት ያስከትላል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 56795፣234426 እና በሌሎች መዛግብት ላይ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

ከላይ ከተገለጸዉ ከሕጉ አቋም አንጻር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 6 መሠረት ዳግመኛ ዳኝነት ተጠይቆ አቤቱታ ቀርቦ እየታየ እያለ በዚያዉ መዝገብ ላይ የተሰጠ ፍርድ በመቃወም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 መሰረት አቤቱታ ቢቀርብ ክርክሩ በምን አግባብ ሊመራ ይገባል? የትኛዉ አቤቱታና ክርክር ቀድሞ ሊመረመር ይገባል? የሚለዉን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነዉም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 መሰረት ለነበረዉ ክርክር ሦስተኛ ወገን የሆነ ሰዉ ሌሎች ሰዎች ተከራክረዉ በተሰጠ ፍርድ መብቴ ተነክቷል በሚል የመቃወም አቤቱታ ማቅረብ የሚችለዉ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

መብቱን ወይም ጥቅሙን የሚነካ የጸና የፍርድ ዉሳኔ ሲኖር ነዉ፡፡ በሌላ በኩል አንድ ተከራካሪ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 6 ላይ እንደተመለከተዉ ዳግመኛ ዳኝነት እንዲታይ አቤቱታ ለማቅረብ የሚችለዉም በዚሁ ድንጋጌ ላይ በተመለከተዉ መሠረት በሐሰት ተዘጋጅቶ የቀረበዉን ሰነድ ወይም ሐሰተኛ የምስክርነት ቃልን ወይም መደለያን ወይም ወንጀል ጠቀስ የሆነ ተግባርን መሰረት በማድረግ የተሰጠ ጸንቶ የሚገኝ የፍርድ ዉሳኔ ሲኖር ነዉ፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 6 መሠረት ዳግመኛ ዳኝነት አቤቱታ ቀርቦ እያታየ እያለ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 መሰረት የፍርድ መቃወሚያ ቢቀርብ በመጀመሪያ ዳግመኛ ዳኝነት የተጠየቀበት አቤቱታ በቅድሚያ ታይቶ ሊወሰን ይገባል፡፡ምክንያቱም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 6(1 እና 2) ስር የተደነገጉትን መስፈርቶች የሚያሟላ እና ዳግመኛ ዳኝነት የተጠየቀበት አዲስ የተገኘዉ ማስረጃ ዳግመኛ ዳኝነት የተጠየቀበትን ፍርድ መሰረታዊ ይዘት የሚነካ (Substantially affects the merit of the case) ስለሚሆን የፍርድ ዉሳኔዉ ሊለወጥ ስለሚችል ዳግመኛ ዳኝነት ሊታይ ይገባል ከተባለ በኋላ የሚሰጠዉን የመጨረሻ ዉሳኔ ዉጤት መጠበቅ ስለሚገባ እና ዉሳኔዉ የሚለወጥ ከሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 መሠረት መቃወሚያ የሚቀርብበት የፍርድ ዉሳኔ ስለማይኖር ነዉ፡፡

ከላይ ከተገለጸዉ አንጻር የያዝነዉን ጉዳይ ስንመለከት የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተጠሪዎች መካከል የነበረዉን ክርክርና የቀረበዉን ማስረጃ መርምሮ 2ኛ ተጠሪ ከይዞታቸዉ ዉጭ ያለ ትርፍ ቦታ የራሳቸዉ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ እንዳላቀረቡ ማረጋገጡን ገልጾ 2ኛ ተጠሪ ትርፍ የያዙትን 1032 ካሬ ሜትር ለ1ኛ ተጠሪ ለቀዉ ሊያስረክቡ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ ከዚህ በኋላ 2ኛ ተጠሪ አዲስ ማስረጃ አግኝቻለሁ በማለት ዳግመኛ ዳኝነት እንዲታይላቸዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 6 መሰረት አቤቱታ አቅርበዉ ፍርድ ቤቱ ዳግመኛ ዳኝነት ሊታይ አይገባም በማለት የ2ኛ ተጠሪን አቤቱታ ዉድቅ በማድረጉ 2ኛ ተጠሪ ለዚህ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርበዉ ክርክሩ እየታየ እያለ የአሁን አመልካች 2ኛ ተጠሪ 1032 ካሬ ሜትር ይዞታ ለ1ኛ ተጠሪ ያስረክቡ ተብሎ የተሰጠዉ ዉሳኔ መብቴን ይነካል በሚል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 መሠረት አቤቱታ አቅርቧል፡፡በዚህ መሠረት አመልካች የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ ካቀረበና የግራ ቀኙ ክርክር ከተሰማ በኋላ 2ኛ ተጠሪ ዳግመኛ ዳኝነት ሊታይ ይገባል አይገባም የሚል ጭብጥ ላይ በፌዴራል ሰበር ችሎት እየታየ ያለዉ ክርክር እልባት እስከሚያገኝ ድረስ በአመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 መሰረት በቀረበዉ አቤቱታ መነሻ እየተደረገ ያለዉ ክርክር ለጊዜዉ ታግዶ እንዲቆይ ጠይቀዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም ይህንን ጥያቄ ተቀብሎ አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 መሠረት ባቀረበዉ አቤቱታ መነሻ እየታየ ያለዉ ክርክር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 197 መሠረት ለጊዜዉ ታግዶ እንዲቆይ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡የስር ፍርድ ቤት በዚህ መልኩ ትእዛዝ በመስጠት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 6 መሠረት ዳግመኛ ዳኝነት ሊታይ ይገባል ወይስ አይገባም በሚል ጭብጥ ላይ ሰበር ችሎት የመጨረሻ ዉሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 መሠረት ባቀረበዉ አቤቱታ መነሻ እየታየ ያለዉ ክርክር ታግዶ እንዲቆይ ትእዛዝ መስጠቱ የክርክሮች አመራር ቅደም ተከተል የጠበቀ ስለሆነ ሥነ ሥርዓታዊ ነዉ፡፡

ሆኖም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁጥር 116118 ላይ በቀን 27/03/2009ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ የስር ፍርድ ቤት ዳግመኛ ዳኝነት ሊታይ አይገባም በማለት የሰጠዉን ዉሳኔ በመሻር ዳግመኛ ዳኝነት ሊታይ ይገባል በማለት ጉዳዩን ለስር ፍርድ ቤት በመመለስ ዉሳኔ ከሰጠ በኂላ የስር ፍርድ ቤት መዝገቡን አንቀሳቅሶ በቀን 23/02/2010ዓ/ም በዋለዉ ችሎት በሰጠዉ ብይን የአሁን አመልካች በተገቢዉ ሥነ ሥርዓት ሕግ አግባብ አቤቱታ በማቅረብ በክርክሩ ተካፋይ እንዲሆን መወሰኑም ሆነ አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 41 መሰረት በክርክሩ ጣልቃ በመግባት ለመከራከር ያቀረበዉን አቤቱታ መቀበሉ ሥነ ሥርዓት ሕጉ ስለክርክር አመራር የዘረጋዉን ሥርዓት የተከተለ አይደለም፡፡ምክንያቱም በመ/ቁጥር 186581 ላይ በቀን 24/03/2006ዓ/ም ተሰጥቶ በነበረዉ የፍርድ ዉሳኔ ላይ ዳግመኛ ዳኝነት ይታይልኝ አቤቱታ ቀርቦ በሰበር ሰሚ ችሎት ዳግመኛ ዳኝነት ሊታይ ይገባል ተብሎ ተወሰነ እንጂ በመዝገቡ ላይ በቀን 24/03/2006ዓ/ም የተሰጠዉ ፍርድ ጸንቶ ስለሚገኝ ዉሳኔ በተሰጠበት ጉዳይ ላይ አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 41 መሠረት ጣልቃ ገብቶ የሚከራከርበት ሥነ ሥርዓታዊ አግባብ የለም፡፡በተጠሪዎች መካከል በሚደረግ ክርክር መነሻ በሚሰጥ ዉሳኔ አመልካች መብቱ ወይም ጥቅሙ የሚነካበት ከሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 መብቱን ወይም ጥቅሙን ማስከበር የሚችለዉ በ2ኛ ተጠሪ በቀረበዉ የዳግም ዳኝነት አቤቱታ ላይ የመጨረሻ ዉሳኔ ከተሰጠ በኂላ ዉሳኔዉ የአመልካችን መብት ወይም ጥቅም የሚነካ ሲሆን ነዉ፡፡

በመሆኑም የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች አስቀድሞ በመዝገቡ ላይ የተሰጠዉን ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 መሠረት በመቃወም ባቀረበዉ አቤቱታ መነሻ የተደረገዉን ክርክር 2ኛ ተጠሪ ባቀረቡት የዳግም ዳኝነት አቤቱታ መነሻ በተጠሪዎች መካከል የሚደረገዉ ክርክር በፍርድ እስከሚወሰን ድረስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 197/2 መሰረት አግዶ ማቆየት ወይም በቀጠሮ እንዲቆይ ማድረግ ሲገባዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 41 ስር የተደነገገዉን ሥነ ሥርዓት አለአግባብ በመጠቀም አመልካች በክርክሩ ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር በማድረግ ዉሳኔ መስጠቱ የአመልካችን ሥነ ሥርዓታዊ መብት ሊያጠብ የሚችል የክርክር አመራር ነዉ፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙ ተከራካሪ በሆኑበት በሰ/መ/ቁጥር 213741 ላይ የአሁን አመልካች 1ኛ ተጠሪ ሆኖ ተከራክሮ በተሰጠ ዉሳኔ የአሁን 2ኛ ተጠሪ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 6 መሠረት ባቀረቡት ዳግም ዳኝነት ይታይልኝ አቤቱታ መነሻ በሚደረግ ክርክር የአሁን አመልካች ጣልቃ እንዲገባ መደረጉ ሥነ ሥርዓታዊ ስላልሆነ ከክርክሩ ዉጭ መደረግ ሲገባ የአሁን አመልካች ያቀረበውን መከራከሪያ እና ማስረጃ መነሻ በማድረግ አስቀድሞ የተሰጠውን ውሳኔ በመሻር በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የክርክር አመራር ስሕተት የተፈጸመበት ነዉ በማለት ወስኗል፡፡ *ምን እንኳን አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 41 መሠረት በክርክሩ ጣልቃ ገብቶ ተከራክሮ የነበረ ቢሆን በመጨረሻም በሰ/መ/ቁጥር 213741 ላይ በተሰጠዉ ዉሳኔ አመልካች በክርክሩ ተካፋይ እንዲሆን መደረጉ ስህተት ነዉ*

ተብሎ ይህንን ስህተት የሚያርም ፍርድ በመስጠቱ ምክንያት አመልካች በክርክሩ ተካፋይ እንደነበረና እርሱ ተከራክሮ በጉዳዩ ላይ እርሱን የሚመለከት የመጨረሻ ዉሳኔ እንደተሰጠ ሊቆጠር አይገባም፡፡

ሲጠቃለል 1ኛ ተጠሪ በ2ኛ ተጠሪ ላይ ክስ የመሠረቱት 2ኛ ተጠሪ ከራሳቸዉ ይዞታ ጋር ይዞታዬን ቀላቅለዉ ስለያዙ አለአግባብ የያዙትን ይዞታዬን ይልቀቁልኝ በሚል ነዉ፡፡ይህንን ክስ ተከትሎ የተደረገዉ ክርክር ተሰምቶ የተሰጠዉ የፍርድ ዉሳኔ በየደረጃዉ ባሉ ፍርድ ቤቶች ታይቶ በመጨረሻም በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 213741 ላይ በቀን 04/02/2015ዓ/ም በተሰጠ የፍርድ ዉሳኔ የጸናዉ ዉሳኔ አስቀድሞ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 186581 ላይ በቀን 24/03/2006 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ ሲሆን ይህም ዉሳኔ የአሁን አመልካች ጣልቃ ገብቶ በተከራከረበት የተሰጠ ዉሳኔ ባለመሆኑ በዚህ ዉሳኔ ላይ 2ኛ ተጠሪ ከራሳቸዉ ይዞታ ጋር ቀላቅለዉ የያዙትን ይዞታ ለ1ኛ ተጠሪ ይልቀቁ በሚል የተወሰነዉ መብቴን ወይም/እና ጥቅሜን ይነካል ብሎ ካመነ አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 መሰረት ፍርዱን በመቃወም ለመከራከር ሥነ ሥርዓታዊ መብት አለዉ፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካችን አቤቱታ ከዚህ አንጻር በማየት ግራ ቀኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሠረት አከራክሮ ሕግን መሠረት ያደረገ ዉሳኔ መስጠት ሲገባዉ አመልካች አስቀድሞ በክርክሩ ተካፋይ ነዉ በማለት ዉድቅ ማድረጉ በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት ጥበቃ የተደረገለትን የአመልካችን ፍትህ የማግኘት መብት የነፈገ በመሆኑ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሀ) እና 10(1/ሀ) መሠረት ሊታረም የሚገባዉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ ብለናል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## <u>ዉሳኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 186581 ላይ በቀን 22/06/2015 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 305704 ላይ በቀን 29/09/2015 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 መሰረት ተሽረዋል፡፡

2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መዝገቡን በማንቀሳቀስ አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 መሰረት ያቀረበዉን አቤቱታ ተቀብሎ በሥነ ሥርዓት ሕጉ መሠረት የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ ሕግን መሠረት ያደረገ ዉሳኔ እንዲሰጥ በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/2 መሰረት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡

3. በዚህ ችሎት የወጣ ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## <u>ትዕዛዝ</u>

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡የስር ፍ/ቤት መዝገብ ይመለስ፡፡
- በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠዉ እግድ ተነስቷል፤ይጻፍ፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ/ጋ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የሰ.መ.ቁ.249083

ጥቅምት 06 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች፡.....1. ብርሃኑ አመነዉ

2. በእዉቀት በላይ

3. ቀነዓ ቂጣታ

4. ብርሃኑ መንግስቱ

5. ማርታ ተካ

አመልካች፡ ........አቶ መኩሪያ ነጋሽ - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡..............አቶ ያዘዉ ነጋሽ - የቀረበ የለም

ይህ መዝገብ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

**ፍርድ**

ይህ የገጠር መሬት ክርክር የተጀመረዉ በአማራ ክልል በሰሜን ሸዋ ዞን በምንጃር ሸንኮራ ወረዳ ንዑስ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች የሥር ከሳሽ፣ የአሁን ተጠሪ የሥር ተከሳሽ ሆኖ ሲከራከሩ ነበር። ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ አመልካች የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.03-14207 ሚያዚያ 16 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ።

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ የአሁን አመልካች በሥር ፍ/ቤት ባቀረቡት የክስ አቤቱታ፡ በዘወልዴ ቀበሌ ዉስጥ የሚገኘዉን 0.3092 ሄክታር መሬት አዋሳኝ በመጥቀስ ለእርሻ የሚጠቀምበትን መሬት ተከሳሽ ይዞታዬን ለመንጠቅ በማሰብ 15 እግር ባህር ዛፍ በመቀረጥ መሬቱን ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ

ስለያዘብኝ ይዞታዬን ለቆ እንዲያስረክበኝ እንዲሁም የባህር ዛፉን ግምት ብር ሀያ ሺህ እንዲከፍለኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

የአሁን ተጠሪ በዚህ ክስ ላይ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያነሳ ቢሆንም ፍ/ቤቱ በብይን ዉድቅ ያደረገ ሲሆን፣ በፍሬ ነገር መልስ በይዞታዉ ላይ በአመልካች ፈቃድ ቤት፣ አጥር፣ አትክልት ዛፎች አልምቼበታለሁ፣ አመልካች ሳይቃወመኝ የሰራሁትና ያፈራሁት ንብረት ባለቤት ስለሆንኩኝ ክሱ ተቀባይነት የለዉም፤ ባህር ዛፉን የቆረጠዉ ተጠሪ ሳልሆን የመብራት ሃይል መ/ቤት በመሆኑ እኔ ሊጠየቅ አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ የወረዳዉ ፍ/ቤት የሰዉ ምስክሮችን በመስማትና ማስረጃ በመመርመር በሰጠዉ ዉሳኔ የአከራካሪዉ ይዞታ ባለይዞታ ተጠሪ መሆኑን በግራ ቀኙ የታመነና በማስረጃም የተረጋገጠ ሲሆን አመልካች ከዚህ መሬት ዉስጥ የያዘዉ 893 ካ.ሜ ይዞታ መሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ነዉ፤ ተጠሪ ባቀረበዉ ክርክር መሰረት አመልካች ያለእሱ በፈቃድ ወይም እየተቃወመዉ ወይም ሳያዉቀዉ አመልካች በራሱ ፈቃድ በሕገወጥ መንገድ በአመልካች ይዞታ ላይ ቤት መስራቱ እና ባህር ዛፍ ስለመቁረጡ በማስረጃ ያስረዳዉ ነገር የለም፤ ተጠሪ በአመልካች ይዞታ ላይ ቤት የሰራዉ በአመልካች ፈቃድ መሆኑን ተጠሪ በማስረጃ አስረድቷል፡፡ ተጠሪ ባህር ዛፉን ቆርጦ መዉሰዱን በማስረጃ አላስረዳም፡፡ አመልካች ባቀረበዉ ክርክር ተጠሪ ከመሬቱ አጠቃቀም ዉጭ ቤት ሰርቷል ያለዉን በተመለከተ ቅሬታዉን ማቅረብ ያለበት ለወረዳዉ ጽ/ቤት እንጂ ለመደበኛ ፍ/ቤት የሚቀርብ ባለመሆኑ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለዉም፤ ባለመሬቱ ሳይቃወም በሌላ ሰዉ መሬት ላይ ቤት የሰራዉ ሰዉ የሕንጻዉ ባለቤት እንደሚሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1179 (2) ሥር የተመለከተ በመሆኑ፣ ተጠሪ በዚህ ቤት፣ አጥር፣ መጋዘንና ጌሾ እና ግቢ ላይ ባለመብት ናቸዉ በማለት ወስኗል፡፡ የአሁን አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ቅሬታዉን ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እና ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቶቹ ቅሬታዉን ዉድቅ በማድረግ የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች በ13/10/2015 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ ተጠሪ በአመልካች የእርሻ መሬት ላይ የሰራዉ ቤት የእርሻዉ መሬት ተጨማሪ ነገር ባልሆነበት ቤቱ ሲሰራ አልተቃወምክም በሚል ምክንያት የመሬቱም የቤቱም ባለሀብት እንዲሆን መደረጉ የህግ ድጋፍ የለዉም፤ በአማራ ክልል የገጠር መሬት ሕግ መሰረት በእርሻ መሬት ላይ ቤት መስራት እንደማይቻልና ሕገወጥ ድርጊት ሆኖ ሳለ የሥር ፍ/ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ የሕግ አተረጓጎም ስህተት ያለበት ነዉ፣ የሥር ፍ/ቤት በአንድ በኩል ጉዳዩን ለማየት ስልጣን እንደሌለዉ የገለጸ ቢሆንም በሌላ በኩል ደግሞ ጭብጡን ቀይሮ ተጠሪ የቤቱ ባለቤት በማለት ዉሳኔ የሰጠ በመሆኑ ክርክሩ የቤት ባለቤትነትን የሚመለከት ከሆነ ፍ/ቤቱ ስልጣን የለም፤ ስለሆነም የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ ተሽሮ ተጠሪ መሬቱን እንዲያስረክበኝ እንዲወሰንልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ይህ ሰበር ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣የሥር ፍ/ቤት አመልካች ሳይቃወሙ ተጠሪ ስፋቱ 893 ካ.ሜ የእርሻ መሬት ላይ ቤት መጋዘን እና አጥር ስለሰሩ እንዲሁም ጌሾ ስላለሙ የንብረቱ ባለቤት ስለሆኑ ይዞታዉን ሊለቁ አይገባም ተብሎ የአመልካች ክስ ዉድቅ የተደረገበትና በየደረጃዉ ያሉት

ፍ/ቤቶች ዉሳኔዉን ማጽናታቸዉ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ.1179፣ ከአማራ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጁ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 32፣ ከኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40 (4)፣ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ. 36638 እና 30101 ላይ ከሰጠዉ የሕግ ትርጉም አንጻር መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ሲባል የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ያዘዘዉ ቢሆንም ተጠሪ መጥሪያ ደርሷቸዉ ባለማቅረባቸዉ መልስ የመስጠት መብታቸዉ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ሰበር ችሎት የአመልካች የሰበር አቤቱታ እና ለቅሬታዉ መነሻ ከሆኑት የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔዎች አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ ለክርክር መነሻ የሆነዉ እና የአሁን ተጠሪ ቤት፣ መጋዘን፣ አጥር የሰራበት ጌሾ የተከለበት ስፋቱ 893 ካ.ሜ ይዞታ የአመልካች ይዞታ መሆኑን ያላከራከረና በማስረጃም የተረጋገጠ ጉዳይ ነዉ፡፡ እንዲሁም የሥር ፍ/ቤት በማስረጃ ካረጋገጠዉ ፍሬ ነገር መረዳት እንደሚቻለዉ የአሁን ተጠሪ በዚህ ይዞታ ላይ እነዚህን ንብረቶች ሲያፈራቸዉ በአመልካች ፈቃድ እና ሳይቃወም መሆኑን ነዉ፡፡ ከዚህ አንጻር አመልካች ባቀረበዉ ቅሬታ የገጠር እርሻ መሬት ላይ ተጠሪ እነዚህን ንብረቶች ያፈራቸዉ በአመልካች ፈቃድና ያለተቃዉሞ ስለሆነ ተጠሪ በንብረቶቹ ላይ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1179 ድንጋጌ መሰረት ባለህብት ይሆናል ተብሎ የተወሰነዉ የአማራ ክልል የገጠር መሬት አዋጅ እና የኢፌዴሪ ሕገ መንግስት የሚቃረን ስለሆነ ተጠሪ ይዞታዬን ለቆ እንዲያስረክበኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

እንደሚታወቀዉ የአማራ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 11 እንደሚደነግገዉ የገጠር መሬት በይዞታ የሚገኝበት አግባብ ስልጣን ካለዉ የመንግስት አካል በድልድል፣ በዉርስ ወይም በስጦታ ብቻ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ይህም ከኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40 (4) ድንጋጌ ሥር የአርሶ አደሮች መሬት የማግኘት መብት ጋር የሚጣጣም ሆኖ እናገኛለን፡፡ በሌላ በኩል ባለመሬቱ ሳይቃወም በሌላ ሰዉ መሬት ሕንጻ የሰራ ሰዉ የዚሁ ሕንጻ ባለህብት እንደሚሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1179 (1) ሥር ተደንግጓል፡፡ በዚህ ሁኔታ ባለይዞታዉ ያለዉ መብት በዚህ ድንጋጌ በንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) ሥር ተመልክቷል፡፡ ከዚህ አንጻር በክርክሩ በተጠቀሰዉ ከተማ ዉስጥ የሚገኝ ይዞታ ላይ ባለይዞታዉ ሳይቃወም በሌላ ሰዉ የመሬት ይዞታ ላይ ሕንጻ የሰራ ሰዉ የዚሁ ሕንጻ ባለህብት እንደሚሆን ይህን ድንጋጌ በመተርጎም ይህ ሰበር ችሎት በሰ.መ.ቁ.36638 ላይ አስገዳጅ ሕግ ትርጉም ዉሳኔ የሰጠ ሲሆን፣ በሌላ ሰዉ የመሬት ይዞታ ላይ በባለይዞታዉ ፈቃድ ሕንጻ የሰራ ሰዉ የሕንጻዉን ግምት ተቀብሎ ሕንጻ ለማስረከብ እንደማይገደድ በሰ.መ.ቁ.30101 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም መስጠቱን ማየት ይቻላል፡፡

በዚህ አግባብ አሁን የተያዘዉ ጉዳይ ሲታይ ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት ባቀረበዉ ክርክር አከራካሪዉ ይዞታ ላይ እነዚህን ንብረቶች ሳለማ አመልካች ፈቃዶና ሳይቃወም ስለፈራሁኝ፣ የንብረቶቹ ባለህብት ሊሆን ይገባል በማለት የተከራከረ ሲሆን፣ የሥር ፍ/ቤቶችም ይህን የተጠሪን ክርክር በመቀበል መወሰናቸዉን መዝገቡ ያሳያል፡፡ ይሁን እንጂ ከፍ ሲል ከተጠቀሰዉ የህግ ድንጋጌ አንጻር እንደጭብጥ ተይዘዉ አግባብነት ባለዉ ማስረጃና ሕግ ተጣርቶ መወሰን የሚገባቸዉ ጉዳዮች

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

መኖራቸዉን ችሎቱ ተገንዝቧል፡፡ በዚህ መሰረት አመልካች ባቀረበዉ ክስ የጠየቀዉ ዳኝነት ተጠሪ መብት ሳይኖረዉ በእርሻ ይዞታዬን በመያዝ ንብረት ስለፈራበት ይዞታዬን ለቆ እንዲያስረክበኝ የሚል እንጂ ተጠሪ የእርሻ መሬቱን አጠቃቀም በመቀየር ቤት የሰራበት በመሆኑ ይህ ድርጊት ሕገወጥ ስለሆነ በዚህ ምክንያት ይዞታዉን እንዲለቅልኝ የሚል አይደለም፡፡ አመልካች አጥብቆ የሚከራከዉ ተጠሪ መብት ሳይኖረዉ ይዞታዬን ስለያዘብኝ እንዲለቅልኝ የሚል እንጂ የመሬቱን አጠቃቀም ስለቀየረ ብቻ እንዲለቅልኝ የሚል ባልሆነበት የሥር ፍ/ቤት የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ በአግባቡ መገንዘብ ሲገባዉ የአመልካች ክስ በፍ/ቤት የሚታይ አይደለም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ የሕግ ድጋፍ የለዉም፡፡

በሌላ በኩል የሥር ፍ/ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም ካለ ደግሞ በፍሬ ነገር ክርክር ዉሳኔ መስጠት ስለማይችል መዝጋት ይገባዉ ነበር እንጂ በአንድ በኩል ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለዉም እያለ በሌላ በኩል ደግሞ የፍሬ ነገር ክርክር በማየት ተጠሪ በይዞታዉ ላይ ንብረቶችን ሊያፈራ የቻለዉ በአመልካች ፈቃድና ያለተቃዉሞ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1179 መሰረት ተጠሪ የንብረቶቹ ባለሀብት ነዉ በማለት የደረሰበት ድምዳሜ እርስ በርሱ የሚጋጭ በመሆኑ ተቀባይነት የለዉም ብለናል፡፡ የሥር ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ ሰምቶ ለመወሰን የሚከለክለዉ ነገር የለም፣ ስልጣን አለዉ ብለናል፡፡

ስለሆነም ተጠሪ በአመልካች ፈቃድና ያለተቃዉሞ በአከራካሪዉ የእርሻ መሬት ላይ ቤት፣ መጋዘን እና አጥር መስራቱ እንዲሁም ጌሾ መትከሉ ከአማራ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ አንጻር ሲታይ እነዚህን ንብረቶች በይዞታዉ ላይ ማፍራቱ ተጠሪ ባለይዞታ እንዲሆን መብት የሚሰጠዉ ነዉ ወይስ አይደለም? አከራካሪዉ ይዞታ በአዋጁ አንቀጽ 32 መሰረት ለመኖሪያ ቤት መስሪያነት የተፈቀደ ነዉ ወይስ አይደለም? እንዲሁም ተጠሪ በገጠር የእርሻ ይዞታ ላይ በአመልካች ፈቃድና ያለተቃዉሞ ቤት እና ሌሎች ንብረቶችን ማፍራቱ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1179 መሰረት የንብረቶቹ ባለሀብት ይሆናል ተብሎ ይዞታዉን ይዞ መቀጠል ይችላል ወይስ አይችልም? ከፍ ሲል ከተጠቀሰዉ የክልሉ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ እና የኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንጻር ሲታይ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1179 በገጠር መሬት ላይ ተፈጻሚነት አለዉ ወይስ የለዉም? የሚሉት ነጥቦች እንደጭብጥ ተያዘዉ ተጣርተዉ ዉሳኔ ሊሰጥባቸዉ የሚገቡ ጉዳዮች ነበሩ፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች የግራ ቀኙን ክርክር መሰረት በማድረግ አግባብነት ያላቸዉን ጭብጦች በመያዝ ጉዳዩን አጣርቶ መወሰን ሲገባቸዉ ይህን ሳያደርጉ የሰጡት ዉሳኔ ከፍ ሲል የተጠቀሱትን የሕግ ድንጋጌዎች፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.136፣ 264፣ 327 (3)፣ 345 እና 246-249 ድንጋጌዎች ይዘትና ዓላማ እንዲሁም ይህ ሰበር ችሎት የሰጠዉን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሚቃረን በመሆኑ ተቀባይነት የለዉም፡፡ በመሆኑም ይህ ሰበር ችሎት በኢፌዴሪ ሕግ መንግስት አንቀጽ 80 (3) (ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2 (4) (ሸ) እና 10 (1) (ሐ) መሰረት ከተሰጠዉ ስልጣን አንጻር አመልካች ያቀረበዉ ቅሬታ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን የሚያመለክት ስለሆነ ቅሬታዉ ተቀባይነት የለዉ ነዉ ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች ከፍ ሲል በተጠቀሰዉ አግባብ የግራ ቀኙን ክርክር መነሻ በማድረግ ጭብጦችን በመያዝ በማጣራት ተገቢ ነዉ ያሉትን ዉሳኔ መስጠት ሲገባቸዉ፣ ባንድ በኩል ይህን

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ጉዳይ ለማየት ስልጣን እያላቸዉ ስልጣን የለንም በማለት በሌላ በኩል በፍሬ ነገር ክርክር ላይ ዉሳኔ መስጠታቸዉ ተገቢ ጭብጥ ሳይዙ ባልተጣራ ጉዳይ ላይ የሰጡት ዉሳኔ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ዉሳኔ**

1. የምንጃር ሸንኮራ ወረዳ ንዑስ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ.0177005/14 በ16/2/2015 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.0139907 በ26/5/2015 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ እና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት 03-14207 በ20/8/2015 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የምንጃር ሸንኮራ ወረዳ ንዑስ ወረዳ ፍ/ቤት በፍርድ የዘጋዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ በፍርድ ሐተታዉ በተመለከቱትን ጭብጦች በመያዝ ከወረዳዉ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ተጣርቶ ማስረጃ እንዲቀርብ በማድረግ እንዲሁም አግባብነት ባለዉ ማስረጃ በማጣራት ቀደም ሲል የቀረበዉን ማስረጃ በመመርመር ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ እንዲሰጥበት በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9 (2) መሰረት ተመልሶለታል፡፡
3. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
4. ግራ ቀኙ የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

**መ/ዐ**

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የሰ/መ/ቁ 249149
ጥቅምት 06 ቀን 2017 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-**

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

ሠናይት አድነው

ሀፊዝ አባ ጀማል

**አመልካች፡-** ዙሚናስ ትሬዲንግ ኃላ/የተ/ግ/ማህበር

**ተጠሪ፡-** 1. ዙሚናስ ትሬዲንግ ኃላ/የተ/ግ/ማህበር

2. ፈለማ ኮንስትራክሽን ኃላ/የተ/ግ/ማህበር

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**<u>ፍርድ</u>**

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሰኔ 14 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 244518 በቀን 21/09/2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ጉዳዩ በአፈጻጸም ክርክር የቀረበ መቃወሚያን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን በስር ፍርድ ቤት አመልካች መቃወም አመልካች 1ኛ ተጠሪ የፍርድ ባለመብት እና 2ኛ ተጠሪ የፍርድ ባለዳ ሆነው ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እንደሚያስገነዝበው የአፈጻጸም ክርክሩ የተጀመረው 1ኛ ተጠሪ የፊኒሺንግ ስራዎች ክፍያ አልተከፈለኝም በሚል ባቀረቡት ክስ የተወሰነላቸውን ገንዘብ ለማስፈጸም የ2ኛ ተጠሪ ንብረት የሆነውን በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ወረዳ 13 የሚገኝ የቤት ቁጥሩ 9999 የሆነ በካርታ ቁጥር የካ/190220/08 የሚታወቅ ንብረት ለፍርድ ቤቱ አቅርበው ፍርድ ቤቱ በንብረቱ ላይ የእግድ እና የሀራጅ ትእዛዝ መስጠቱን ተከትሎ አመልካች ጥቅምት 29 ቀን 2015 ዓ.ም ባቀረበው የመቃወም አቤቱታ ንብረቱን አመልካች የካቲት 10 ቀን 2014 ዓ/ም በፌዴራል ሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ በተደረገ ውል ንብረቱ ዕዳ እና እገዳ እንደሌለው ከክፍለ ከተማው መሬት ልማት አስተዳደር ጽ/ቤት አረጋግጠው ከ2ኛ ኛተጠሪ ላይ በብር 26,000,000.00 /ሃያ ስድስት ሚሊዮን ብር/ የተረከቧቸው መሆኑን በመግለጽ በአመልካች ንብረት ላይ የተጀመረው አፈጻጸም እንዲቆም አመልክተዋል፡፡

1ኛ ተጠሪ ህዳር 19 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት አስተያየት የቤቱ ስም ሀብት በተጠሪ ስም መሆኑን፤ አመልካች የካቲት 10 ቀን 2014 ዓ.ም ንብረቱን ሲገዛ ዕዳና እገዳ እንደሌለው አረጋግጦ የገዛ ስለመሆኑ ያቀረበው ማስረጃ የለም፤ ንብረቱ በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሥራ ክርክር ችሎት በመ/ቁጥር 176093 በቀን 2/5/2014ዓ.ም እንዲሁም በዚህ ችሎት ታግዶ እያለ አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ተገቢነት የለውም በማለት አስተያየት አቅርቧል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የግራቀኙን ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ አመልካች ንብረቱን የገዛው የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 176093 የተሰጠ እግድ እያለበት በመሆኑ እና የንብረቱ የይዞታ ማረጋገጫ የሚገኘው በ2ኛ ተጠሪ ስም ነው በማለት የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ አድርጓል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱ ይግባኙን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

አመልካች ሰኔ 14 ቀን 2015ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይህን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ሲሆን ይዘቱም አመልካች የካቲት 10 ቀን 2014 ዓ.ም በፌደራል ሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ፊት በተደረገ የሽያጭ ውል ንብረቱ ምንም አይነት ዕዳ እና እገዳ እንደሌለበት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ከክፍለ ከተማው መሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት አጣርተው ከ2ኛ ተጠሪ መግዛታቸውን፤ ውሉንም ከአምስት ቀን በኃላ ከቤቱ ፋይል ጋር እንዲያያዝ ማድረጋቸውን፤ በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 176693 የተሰጠው እግድ እነ አቶ ግርማ ማንደፍሮን የሚመለከት እንጂ 1ኛ ተጠሪን የሚመለከት ስላልሆነ 1ኛ ተጠሪ አመልካች የፈጸሙትን ግዥ እንዲቃወም የሚያስችል መብት የማይፈጥርላቸው መሆኑን፤ የእግድ ትዕዛዙ የተሰጠውም የካቲት 17 ቀን 2014 ዓ.ም አመልካች ቤቱን የካቲት 10 ቀን 2014 ዓ.ም ከገዙ በኃላ መሆኑን፤ እግዱን ለማስፈጸም ክፍያ ለክፍለ ከተማው የተከፈለው መጋቢት 04 ቀን 2014 ዓ.ም መሆኑን ፤ የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት በከ/መ/ቁ 173079 ላይ ከፍርድ በፊት የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት አስመልክቶ የሚሰጥ የንብረት ማስከበር ወይም የእግድ ትእዛዝ ከፍርድ የመነጨ መያዣ ብሎም የቅድሚያ መብትን አያቋቁምም በማለት አስገዳጅ ፍርድ የሰጠበት በመሆኑ አመልካች በንብረቱ ላይ የተሻለ መብት ስላለው አፈፃፀሙ ሊቀጥል አይገባም የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ በሰበር ችሎት ተመርምሮ አመልካች እግድ ይነሳልኝ በማለት ባቀረበው አቤቱታ እግድ እንዲነሳለት የጠየቀውን ቤት በተጠሪዎች የግራ ቀኝ ክርክር የካቲት 17 ቀን 2014 ዓ.ም እግድ ከመሰጠቱ በፊት የካቲት 10 ቀን 2014 ዓ.ም በህጋዊ መንገድ በተደረገው ውል መግዛቱን ባረጋገጠበት ሁኔታ የስር ፍርድ ቤቶች በሌላ ሰው ምክንያት በተባለው ቤት ላይ ጥር 2 ቀን 2014 ዓ.ም የተሰጠውን እግድ መሰረት በማድረግ የተሰጠው እግድ ሊነሳ አይገባም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የሰጡትን ትዕዛዝ አግባብነት ለመመርመር የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

1ኛ ተጠሪም ታህሳስ 18 ቀን 2016 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ ይዘትም ፍርድ እንዲፈፀም ትዕዛዝ የተሰጠበት ቤት ስመ ሀብቱ በ2ኛ ተጠሪ ስም ያለ መሆኑን፤ አመልካች ንብረቱን ሲገዛ ከዕዳ ነፃ መሆኑን አረጋግጦ ስለመግዛቱ የቀረበ ማስረጃ የሌለ በመሆኑ አመልካች በሕግ አግባብ የተቋቋመ የቅድሚያ መብት ስለሌላቸው የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ተገቢ ነው የሚል ነው፡፡

2ኛ ተጠሪ በአድራሻቸው ሊገኙ ስላልቻሉ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥሪ ተደርጎላቸው መልስ ስላላቀረቡ መልስ ማቅረብ መብታቸው ጥር 29 ቀን 2016ዓ.ም በተሰጠ ትእዛዝ ታልፏል፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን የሚያጠናክር የካቲት 06 ቀን 2016 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገቡ ጋር እንዲያያዝ ተደርጓል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ፣ ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እና ቅሬታው ለሰበር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ነጥብ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደሚቻለው ለክርክሩ ምክንያት የሆነውንና የ2ኛ ተጠሪን ቤት አመልካች በፍርድ ቤት በወጣ የሀራጅ ትእዛዝ መስጠቱን የካቲት 10 ቀን 2014 ዓ/ም በፌዴራል ሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ በተደረገ ውል ንብረቱ በመግዛት የተረከበ መሆኑን፤ ሆኖም ከዚህ በሃላ 1ኛ ተጠሪ ከ2ኛ ተጠሪ ሊከፈለው የሚገባ ገንዘብ ለማስፈጸም በዚህ ንብረት ላይ አመልካች በግዢ ከተላለፈ በሃላ የካቲት 17 ቀን 2014 ዓ.ም የተሰጠውን እግድ በመቃወም በንብረቱ ላይ የተጀመረው አፈጻጸም እንዲቆም መጠየቁን የሚመለከት ነው፡፡

በመሰረቱ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.418 ድንጋጌ አስፈላጊነት የክርክሩ አካል ያልሆኑና ፍርድ ያላረፈባቸው የ3ኛ ወገኖች ንብረት ሳይረጋገጥ ለፍርድ ማስፈፀሚያነት እንዳይውሉ መከላከል በአንፃሩም የፍርዱን አፈፃፀም ለማስተጓጎል አላግባብ ለሚቀርቡ አቤቱታዎች ተገቢውን እልባት መስጠት መሆኑን ከድንጋጌው አጠቃላይ ይዘት ያስገነዝባል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት በንብረቱ ላይ የተያዘውን አፈፃፀም ለመቃወም የሚቀርበውን አቤቱታ በቂ ባልሆነ ምክንያት አፈፃፀሙን ሆነ ብሎ ለማዘግየት የቀረበ መሆኑን ፍርድ ቤቱ ከተረዳው ውድቅ ሊያደርገው የሚችል መሆኑ በቁጥር 418(1) የተመለከተ በመሆኑ አቤቱታ አቅራቢው ያቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት እንዲያገኝ በቁጥር 418(3) አግባብ ባለይዞታነቱን ለማሳየት ተገቢውን ማስረጃ ሊያቀርብ የሚገባ ሲሆን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.418(3) የአማርኛው ቅጂ ላይ የሚቀርበው ማስረጃ የፅሁፍ ማስረጃ ብቻ ሊሆን የሚገባ መሆኑን የሚያመለክት ቢሆንም አቤቱታ እንደቀረበበት የንብረት አይነት አቤቱታው በሰው ምስክሮችም ጭምር ሊደገፍ እንደሚችል በሰበር መዝገብ ቁጥር 97094 አስገዳጅ የህግ ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይ አመልካች ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ቤት አፈፃፀሙ ሊቀጥልበት አይገባም በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ቁ 418 መሰረት አቤቱታ ያቀረቡበት በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ወረዳ 13 የሚገኝ የቤት ቁጥሩ 9999 የካርታ ቁጥር የካ/190220/08 የሚታወቀው ቤት በ2ኛ ተጠሪ ተመዝግቦ የሚገኝ

ቢሆንም ይህንን ቤት 2ኛ ተጠሪ በሌላ መዝገብ በነበራቸው ክርክር በፍርድ ቤት በተሰጠ ሀራጅ ሽያጭ ትእዛዝ ሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ በተደረገ ውል ንብረቱ አመልካች በመግዛት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የተረከበ መሆኑን እና ከቤቱ ፋይል ጋር እንዲያያዝ ማድረጋቸው በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ሲሆን የአሁን 1ኛ ተጠሪ አመልካችነት ለፍርድ ማስፈጸሚያ በንብረቱ ላይ የእግድ ትእዛዝ የተሰጠው ከዚህ በሃላ የካቲት 17 ቀን 2014 ዓ.ም ነው፡፡ በሌላ በኩል በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 176693 በእነ አቶ ግርማ ማንደፍሮን አመልካችነት ተሰጥቷል የተባለው እግድ በተመለከተ በአመልካች እና በእነ አቶ ግርማ ማንደፍሮን መካከል በሚነሳ ክርክር የሚወሰን በመሆኑ የ1ኛ ተጠሪ መከራከሪያ ሁኖ ሊቀርብ አይችልም፡፡

ስለሆነም የንብረቱ ይዞታ ማረጋገጫ የሚገኘው በ2ኛ ተጠሪ ስም መሆኑን አመልካች በሽያጭ ንብረቱን መረከባቸው እና ከቤቱ ፋይል ጋር እንዲያያዝ መደረጉ ከተረጋገጠ ደግሞ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.418 መሰረት አቤቱታውን ያቀረቡት በቂ ባልሆነ ምክንያት አፈፃፀሙን ንብረቱ የሚገኘው በ2ኛ ተጠሪ ስም በመሆኑ አመልካች የተሻለ የቅድሚያ መብት ያላቸው መሆኑን አላረጋገጡም ሊባል የሚችልበት አግባብ ስለሌለ የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ሆነ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔ ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች መሰረት ያላደረገ በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሁኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 244518 በቀን 21/09/2015 ዓ.ም የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ በማጽናት የሰጠው ውሳኔ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1//ሀ/መሰረት መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ለክርክር ምክንያት የሆነው በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ወረዳ 13 የሚገኝ የቤት ቁጥሩ 9999 የሆነውን ቤት ከእግድ ትእዛዙ በፊት በግዢ የተለለፈ ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት በበቂ ሁኔታ ያረጋገጠ በመሆኑ የካቲት 17 ቀን 2017 ዓ.ም በተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ሊነሳ ይገባል በማለት ተወሰነ፡፡
3. 1ኛ ተጠሪ ከሽያጩ ገንዘብ የሚያቀርቡትን መብት ይህ ውሳኔ አያስቀርም፡፡
4. አመልካችና ተጠሪ በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

እ/ጋ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የሰበር መ/ቁ/249171
ጥቅምት 05 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች፡ ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

ሠናይት አድነው

ሀፊዝ አባጀማል

አመልካች፤ 1. ወ/ሮ ወሰኔ አበራ ቱሉ

2. ወ/ሮ ፋናዬ አበራ

3. ወ/ሮ በላይነሽ አበራ

4. አቶ በለጠ አበራ

ተጠሪ፤ ወ/ሮ የሺ ቱሉ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

**ፍርድ**

ጉዳዩ የአፈጻጸም ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 303784 ግንቦት 22 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የፌደራል የመጀመርያ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት በሰጠው ትእዛዝ ላይ ተፈጽሟል ያሉትን መሠረታዊ የሕግ ስህተት በመጥቀስ በሰበር ታይቶ እንዲታረም የአሁን አመልካቾች ሰኔ 15 ቀን 2015 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡

ጉዳዩ በተጀመረበት የስር የፌደራል የመጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ ከስር 2ኛ ተከሳሽ አቶ አበራ ቱሉ ጋር በነበራቸው ክርክር በተሰጠ ውሳኔ ላይ የአሁን አመልካቾች የፍርድ መቃወም አቤቱታ አቅርበው ወደ ክርክር የገቡ ቢሆንም የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካቾች ያቀረቡትን የመቃወም አቤቱታ ውድቅ በማድረግ ውሳኔ በመስጠቱ የአሁን አመልካቾች ለስር የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረቡት የይግባኝ ቅሬታ መነሻነት ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ በመ/ቁ.189983 ነሐሴ 17 ቀን 2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት አመልካቾች የስር 2ኛ ተከሳሽ የአባታችን ቦታ ነው በማለት አባታቸውም ይኖሩበት በነበረው በአሁን ተጠሪ ይዞታ ላይ ተጠሪ ሳይቃወሙ መኖርያ ቤቶች የሰሩ ስለሆነ አመልካቾች ለሰሩት ቤቶች የቤቱ ባለቤቶች ናቸዉ በመሆኑም ተጠሪ ለአመልካቾች የቤቱን ግምት በመክፈል ቤቱን የማስለቀቅ መብታቸዉ የተጠበቀ ነዉ በማለት የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በመሻር ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ፍርድ መነሻነት ተጠሪ ባቀረቡት የአፈጻጸም አቤቱታ ላይ የስር 2ኛ ተጠሪ እና አመልካቾች ቤቱን እንዲያስረክቧቸዉ የጠየቁ ሲሆን ፍርድ ቤቱ በዋናው ክርክር ይግባኝ ሰሚዉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፍርድ ባለመብት የሆኑት የአሁን ተጠሪ የቤቱን ግምት ከፍለዉ እንዲያስቀሩ በወሰነዉ መሰረት ግምቱን በገለልተኛ አካል ሶልቲዩድ ቨልሽን ኢንጂነሪንግ በተባለ ገማች ድርጅት እንዲሰራለት በማዘዝ ተገምቶ በቀረበው ግምት መሰረት ተጠሪ ከፍለዉ ቤቱን በማስቀረት አፈጻጸሙ በተጀመረዉ አግባብ ይቀጥል ሲል በማዘዝ መዝገቡን ዘግቷል፡፡ በዚህ ተዕዛዝ ላይ ቅር በመሰኘት አመልካቾች ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ ያቀረቡ ቢሆንም ፍርድ ቤቱም የአመልካቾችን የይግባኝ ቅሬታ ውድቅ በማድረግ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.337/1/ መሰረት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም ይህንን የስር ፍርድ ቤት ትእዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ይዘት ባጭሩ፤ ለአመልካቾች ሊከፈል የሚገባው የቤቶቹ የወቅቱ የገበያ ዋጋ ግምት እንጂ በመሀንዲስ ግምት ሊሆን አይገባውም የሥር ፍርድ ቤቶች የአፈፃጸም ትዕዛዝ ከዋናው ውሳኔ ውጪና የህግ ትርጉምን የሚቃረን ነዉ በማለት የሰበር ዉሳኔን ጠቅሰዉ የተሰጠው የአፈፃጸም ትዕዛዝ የአመልካቾችን መብት የሚጎዳና ከፍርዱ ውጪ የተሰጠ የአፈፃጸም ትዕዛዝ በመሆኑ ፍርድ ያረፈባቸው ቤቶች መነሻ ግምት ከቀረበ በኃላ በግልፅ ጨረታ ቀርበው

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በሚያወጡት ዋጋ መሠረት ተጠሪ ለአመልካቾች ከፍለው ቤቶቹን ሊለቁ ይገባል ተብሎ የስር ፍርድ ቤት የአፈፃጸም ትዕዛዝ ተሽሮ ከበቂ ወጪና ኪሳራ ጋር ይወሰንልን የሚል ነው፡፡

የአመልካቾችም አቤቱታ በሰበር ችሎቱ ተመርምሮ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.189983 ነሐሴ 17 ቀን 2010 ዓ.ም ግራ ቀኙን በማከራከር ከሰጠዉ ዉሳኔ አንጻር ለአመልካቾች ሊከፈላቸዉ የሚገባዉ የአከራካሪዎች ቤቶች የገበያ ዋጋ ነዉ ወይስ የግንባታ ዋጋ የሚለዉን ለመመርመር ሲባል የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ታዟል፡፡

ተጠሪ ነሐሴ 22 ቀን 2015 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል ይዘቱም፣ አመልካቾች በሥር ፍ/ቤት በተጠሪ ይዞታ ላይ የተሰሩትን ቤቶች ግምት ስንቃወም ነበር በማለት ያቀረቡት የቅሬታ ነጥብ በስር ፍ/ቤት ያልቀረበ አዲስ ፍሬ ጉዳይ በመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.329 መሰረት ከሥነ-ሥርዓት ዉጪ በመሆኑ በሰበር ደረጃ ሊቀርብ የማይችል መሆኑን፣ አመልካቾቸ ሊከፈለን የሚገባዉ የቤቶቹ የገበያ ዋጋ ግምት ነዉ በማለት ያቀረቡት ክርክር ከሰበር ዉሳኔ መ/ቁ.186461 (ቅጽ25) እና የፍ/ህግ ቁ.1130-1133 ድረስ ያሉ ድንጋጌዎችን የሚቃረን ነዉ ይኸም ቤቶቹ ካሉበት መሬት ተነጥለዉ ለሽያጭ ወይም በጨረታ ለገበያ ሊቀርቡ አይችሉም ቤቶቹ በምን ያህል ወጪ ሊገነቡ እንደሚችሉ ብሄራዊ ባንክ ፍቃድ በሰጣቸዉ የንብረት ገማቾች በሚያወጡት ግምት በመሆኑ መከራከርያዉ አግባብ ያለመሆኑን እና እንዲሁም አመልካቾች በሰበር አቤቱታቸዉ ላይ የጠቀሱት የሰበር ዉሳኔዎች ለጉዳዩ አግባብነት የሌላቸዉ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ትእዛዝ የሚነቀፍ እና መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም ስለሆነም ሊጸና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾች የመልስ መልስ አላቀረቡም፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና የክርክሩ ይዘት በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን ይህ ችሎትም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አኳያ እና ከተገቢው ህግ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡
እንደመረመርነዉም በዋናው መዝገብ አመልካቾች ተጠሪ ሳይቃወሙ የሰሩትን ቤት ተጠሪ ግምት ከፍለው እንዲያስቀሩ የተሰጠ ውሳኔ መኖሩ አከራካሪ አይደለም አመልካቾች እየተከራከሩ ያሉት የሥር ፍርድ ቤቶች ፍርድ ያረፈባቸውን ቤቶች የገበያ ዋጋ እንጂ ዝቅተኛ የመሀንዲስ ግምት ማለትም ቤቶቹ የተሰሩበት ዋጋ ተከፍሎ ልቀቁ በማለት የሰጡት የአፈፃጸም ትዕዛዝ የአመልካቾችን መብት የሚጎዳና ከፍርዱ ውጪ ነዉ የሚል ሲሆን ተጠሪ ደግሞ ሊከፈላቸዉ የሚገባዉ ቤቶቹ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ሲሰሩ የሚያወጡትን ወጪ በመሆኑ ይህ ደግሞ ፍቃድ ባለዉ ባለሙያ ዋጋዉ ተገምቶ የቀረበ በመሆኑ በዚሁ መሰረት ሊከፈላቸዉ የሚገባ ነዉ የሚል ነዉ፡፡ በመሆኑም ምላሽ የሚየሻዉ ጉዳይ ለአፈጻጸም ክርክሩ መነሻ የሆነዉ በዋናዉ መዝገብ ላይ ከተሰጠዉ ዉሳኔ አንጻር ለአመልካቾች ሊከፈላቸዉ የሚገባዉ የአከራካሪዎች ቤቶች የገበያ ዋጋ ነዉ ወይስ የግንባታ ዋጋ ነዉ? የሚል ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 378 (1,2) መሠረት ፍርድ የሚፈጸመዉ እንደ ፍርዱ መሆን እንዳለበት ድንጋጌዉ በግልጽ ያስረዳል፡፡ ይህም ማለት በአስፈጻሚዉ ፍርድ ቤት ሊፈጸም የሚችለዉ በዋናዉ መዝገብ ላይ የተፈረደዉን ፍርድ ብቻ ነዉ ማለት ነዉ፡፡ ከዚህ አኳያ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.103787 (ቅጽ19) ላይ በፍርድ ባለመብት አማካኝነት የተፈረደን ፍርድ ለማስፈጸም የቀረበው የአፈጻጸም የክስ ማመልከቻ ይፈጸም የተባለውን ፍርድ ብቻ መሰረት ሊያደርግ የሚገባ መሆኑን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378'ን በመተርጎም ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም ፍርድ ቤቶች አንድን ፍርድ እንደፍርዱ ይዘት ውጤት ባለው መልኩ ፍርዱን ከማስፈፀም በቀር የፍርዱን ይዘት በመመልከት የፍርዱን ይዘት አድማስ በማጥበብም ሆነ በማስፋት ፍርድን የመተርጎም ስልጣን እንደሌላቸው በሰ/መ/ቁ.152172 (ቅጽ.23) ላይ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 372 እና 378 ጋር አያይዞ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

በሌላ በኩል የአመልካቾች ክርክር ተጠሪ ሳይቃወሙ በይዞታቸዉ ላይ ቤት የሰሩ መሆኑ ተረጋግጦ በፍ/ሕግ ቁ. 1179(1 እና 2) መሰረት የስር ከፍተኛዉ ፍርድ ቤት በዋናዉ መዝገብ ላይ ዉሳኔ የሰጠ ሲሆን በዚህ ድንጋጌ መሰረት ባለመሬቱ ሳይቃወም በሌላ ሰዉ መሬት ላይ ሕንጻ የሠራ የዚሁ ሕንጻ ባለሀብት እንደሚሆን ነገር ግን ከባለመሬቱ ጋር ከተስማሙ ግምቱን ከፍሎ ሕንጻዉን ሊያስለቅቅ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ በዚህ አግባብ አመልካቾች በተጠሪ የመሬት ይዞታ ላይ ቤት በመስራታቸዉ የቤቱ ባለሃብት መሆናቸዉ የተወሰነላቸዉ እንጂ አመልካቾች እንደሚሉት የዉርስ ክርክር ሆኖ የንብረቱ ባለሀብት መሆናቸዉ የተወሰነላቸዉ ባለመሆኑ ቤቱ ያረፈበትን ይዞታ ጨምሮ የመከራከር መብት ህጉ የሚሰጣቸዉ አይደለም፡፡ ይህም ማለት የአመልካቾች የቤቱ ባለቤት መሆን ያለዉ ዉጤት አንድም የሰሩትን ቤት በራሳቸዉ ወጪ አንስተዉ ይዞታዉን መልቀቅ፤ አልያም ደግሞ ግምቱ ተከፍሏቸዉ ይዞታዉን መልቀቅ ነዉ፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች ግምት ተከፍሏቸው ቤቱን እንዲለቁ ውሳኔ የተሰጠ መሆኑ አከራካሪ አይደለም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.40510 (ቅጽ8) ላይ እንዳብራራዉ የገበያ ዋጋ ማለት አንድ ቤት ለገበያ (ለሽያጭ) ቢቀርብ የሚያስገኘዉ ዋጋ ሲሆን ዋጋዉን ለመገመትም ቤቱ የሚገኝበትን አካባቢ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በወቅቱ ክፍፍሉ በሚደረግበት የሚኖረዉን የገበያ ሁኔታ መሆኑን እና የግንባታ ዋጋ ደግሞ ቤቱን ለመስራት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች መግዣ የሚወጣዉን ወጪና ለሰራተኞች የሚከፈለዉን ገንዘብ መሆኑን አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

ስለሆነም አመልካቾች የተወሰነላቸው የሰሩት ቤት ግምት እንዲከፈላቸው እንጂ በወቅታዊ የገበያ ዋጋ እንዲከፈል የተሰጠ ውሳኔ ስለሌለ፣ አመልካቾች ህንጻዉ እንጂ ይዞታዉ የእነርሱ ስላልሆነ እና በአጠቃላይ የቤቱ የጋራ ባለሀብት ስላልሆኑ ግምቱ ሊከፈላቸው የሚገባው በቤቱ ግንባታ ላይ በወቅቱ ያወጡትን ወጪ ነው በማለት የስር የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ደምድሞ አከራካሪዎቹን ቤቶች በባለሙያ አስገምቶ በቀረበዉ ግምት መሰረት ይከፈል በማለት የአፈጻጸም ትእዛዝ መስጠቱ እና የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንን ትእዛዝ በማጽናት ትእዛዝ መስጠቱ ህጉን እና የሰበር ሰሚ ችሎት በተለያዩ መዝገቦች ላይ የሰጣቸውን አስገዳጅ የህግ ትርጉሞች መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት እና የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡

በተጨማሪ አመልካቾች ለክርክራቸዉ መሰረት አድርገው የጠቀሷቸው የሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔዎች የዉርስ ክርክርን የጋራ ንብረት ክርክር ላይ በተሰጠ የአፈጻጸም ተዕዛዝ ላይ የተሰጠ የሰበር ዉሳኔን የሚመለከት እንጂ አመልካቾች ለጠቀሱት ጉዳይ አግባብነት ያለቸዉ ሆነው አልተገኙም፡፡
ሲጠቃለል ክርክሩን በየደረጃዉ የተመለከቱት የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ትእዛዝ ህጉን መሰረት ያደረገ ነዉ ከሚባል በስተቀር በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2/4/ እና 10 ድንጋጌ መሰረት ለሰበር ችሎቱ ከተሰጠዉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የማረም ስልጣን አንጻር በዉሳኔዉ ሊታረም የሚገባ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚባልበት ምክንያት አላገኘንም፡፡ በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 303784 ግንቦት 22 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የፌደራል የመጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 45021 መጋቢት 06 ቀን 2015 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት የሰጠውን የአፈጻጸም ትእዛዝ በማጽናት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡

2. በዚህ ፍርድ ቤት ለተደረገዉ ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

<u>ማስታወሻ</u>፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

3. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ/ጋ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መዝገብ ቁጥር 249194

ጥቅምት 7 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች፡…

1. እትመት አሡፋ
2. ደጀኔ አያንሳ
3. ኑረዲን ከድር
4. መላኩ ካሳዬ
5. ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች፡- ……. አቶ ተፈሪ ተሾመ

ተጠሪ ፡- ………. ወ/ሮ ጀምበር ውብሸት } አልቀረቡም (VC አይሰማም)

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል።

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 06737 ግንቦት 2 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ብይንና እና ትዕዛዝ እንዲሁም የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 19719 የካቲት 20 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል አመልካች ግንቦት 28 ቀን 2015 ዓ.ም ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ መነሻነት ነው፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የክርክሩ አመጣጥ ከሥር ፍርድ ቤት መዝገብ እንደተረዳነው አመልካች ከሳሽ ፤ ተጠሪ ዳግሞ ተከሳሽ በሰበር ክርክሩ የሌሉት ወ/ሮ ጌጠነሽ አየለ ጣልቃ-ገብ ተከራካሪ ነበሩ፡፡ አመልካች ጥር 20 ቀን 2015 ዓ.ም የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረቡት የክስ አቤቱታ ለ7(ሰባት) ዓመታት ከወ/ሮ አልማዝ አየለ በአደራ ተሰጥቷቸው በእጃቸው አድርገው የሚያዙበትንና የኪራይ ገቢውን የሚጠቀሙበት መገኛው ፤ አዋሳኞቹ እንዲሁም ቁጥሩ በክሱ ላይ የተመለከተው ቤት ተጠሪ እንዲጠብቁላቸው ያስቀመጡትን ሰዎች በማባረር እና ቤቱን ሰብሮ በመግባት ቤቱንና በቤቱ ውስጥ ያሉ ንብረቶችን በጉልበት በመያዝ እየተጠቀሙበት እንዳሉ በመግለጽ ተጠሪ በክስ አቤቱታው ውስጥ የተመለከቱ ንብረቶች ላይ የፈጠሩት የሁከት ተግባር እንዲወገድ ፤ ቤት እና ዕቃውን ለቀው እንዲወጡ ፤ በሁከቱ ምክንያት ማግኘት የነበረባቸው የ5 ወራት የኪራይ ገቢ ከነወለዱ ብር 25,070.00(ሃያ አምስት ሺ ሰባ) ፤ ክርክሩ አልቆ ቤቱን እስከሚረከቡት ድረስ ያለው በወር በብር 4,600.00(አራት ሺ ስድስት መቶ) ተሰልቶ እንዲከፈላቸው ፤ በአደራ የተረከቡበትን የቤት ቀሰቁሶች እንዲያስረክቧቸው አሊያም ግምቱ 67,100.00(ስልሳ ሰባት ሺ አንድ መቶ) ብር እንዲከፍሉ እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪም የክስ አቤቱታው ድርሷቸው ለክሱ በሰጡት መልስ የቤቱ ባለቤት የነበሩት ሟች ወ/ሮ አልማዝ አየለ ከ1981 ዓ.ም ጀምሮ ያሳደጓቸው እናታቸው በ2004 ዓ.ም ህይወታቸው ስላለፈ የሟቿ ሕጋዊ ወራሽ ስለሆንኩኝ በቤቱም ሆነ በቤቱ ውስጥ ያሉ ንብረቶች የማዘዝ መብት ያላቸው መሆኑን ፤ አመልካች ሲያዙበት የነበረ በይዞታቸው ሥር መኖሩን ገልፀው የቀረበው ክስ ሀሰት መሆኑን ፤ አመልካች አንድም ቀን በቤቱ አዘው እንደማያውቁ ፤ ከአመልካች ጋር በነበራቸው የትዳር ግንኙነት የፍቺ ውሳኔ እስከተሰጠበት ጊዜ ድረስ እንደቤተሰብ አብሮ ከመኖር ባለፈ አመልካች ሕጋዊ በቤቱ የማዘዝ መብት ያልነበራቸው መሆኑን፤ቤቱ በአደራ አልተሰጠም እንጅ ቢሰጥ እንኳን የቤቱ ባለቤትነት ወይም ባለይዞታ የማያደርጋቸው መሆኑን ተከራክረዋል፡፡ በሰበር ክርክሩ የሌሉት ወ/ሮ ጌጠነሽ አየለ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት ሟች ወ/ሮ አልማዝ አየለ ለእሳቸው እና ለተጠሪ እንደተናዘዙላቸው ገልፀው አመልካች ያቀረቡት ክስ ውድቅ ሆኖ ሟች ከሞቱበት ጊዜ አንስቶ አመልካች ሲጠቀሙበት የነበረው የኪራይ ገቢ ተሰልቶ እንዲከፈላቸው ፤ እንዲሁም አከራካሪው ቤት የተጠሪ እና የጣልቃ ገቧ የጋራ ሃብት ነው ተብሎ እንዲወሰን ጠይቀዋል፡፡ አመልካች እና ተጠሪ ለጣልቃ ገብነት አቤቱታው ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ፍርድ ቤቱም የአመልካችን ማስረጃ ሰምቶ መዝገቡን እንደመረመረው፡- ቀርበው የተሰሙት የአመልካች ምስክሮች ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ ቤቱን እንዳከራዩዋቸው ቤቱ የአመልካች መሆኑን የገለጹ ቢሆንም አከራካሪው ቤት ለአመልካች በአደራ የተሰጣቸው መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ አልቀረበም፡፡ አመልካች አከራካሪዎቹን ንብረቶች በአደራ ሰጥተውኛል የሚሏቸው ወ/ሮ አልማዝ አየለ በ2004 ዓ.ም መሞታቸው ያልተካደ ሲሆን ተጠሪ እና ጣልቃ-ገብ በንብረቱ ላይ ወራሽነታቸውን ባረጋገጡበት ሁኔታ አመልካች በቤቱ ላይ ከተጠሪ እና ጣልቃ-ገብ የተሸለ መብት ስለሌላቸው ተጠሪ እና ጣልቃ-ገብ በሕጋዊ ውሳኔ ባለመብት ስለሆኑና የተሻለ መብት ያላቸው መሆኑን ስላስረዱ የሁከት ተግባር ፈጽመዋል ሊባል አይችልም፤እንዲሁም አመልካች የሟች ወራሽ መሆናቸው ባልተረጋገጠበት በአደራ ተቀብያለሁ የሚሉት ሌሎች ንብረቶች የመጠየቅ መብት የላቸውም በማለት የአመልካች ክስ ውድቅ አድርጓል፡፡ አመልካች በውሳኔው ባለመስማማት ያቀረቡት የይግባኝ አቤቱታ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 337 መሠረት ውድቅ አድርጎታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይሕን ውሳኔ በመቃወም ሲሆን የአቤቱታው ይዘት፡- ተጠሪ የኑዛዜ ወራሽ መሆናቸውን የሚገልጽ ነው የተባለው በመዝገብ ቁጥር 21264 ላይ የተሰጠው ውሳኔ በማስረጃነት እንዴት እንደቀረበ ካለመታወቁም በላይ አመልካች አስተያየት ያልሰጡት ያለበቂ ምክንያት ተቀባይነት ማግኘቱ ተገቢ አይደለም፡፡ ማስረጃው ተቀባይነት አለው ቢባል እንኳን ለተጠሪ መብት አጎናጽፏል በተባለው ኑዛዜ ላይ ሳያከራክር ሰነዱን ሊስተባበል የማይችል ባለሃብትነትን እንደሚያረጋግጥ ማስረጃ ወስዶ በቤቱ ላይ ሁከት አልፈጠረችም መባሉ በሰበር መዝገብ ቁጥር 27506 ላይ የተሰጠውን አስገዳጅ ውሳኔ የሚፃረር እና ፍትሕ የማግኘት መብትን የሚጥስ ነው፡፡ አመልካች አከራካሪውን ቤት በአደራ የተረከቡት የሟች አልማዝ አየለ ንብረት መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን ተጠሪ አምነው እያለ በእጃቸው አድርገው የሚያዙበትን ንብረት ተጠሪ በኃይል ይዘው ኪራይ መቀበላቸው በምስክር በተረጋገጠበት ይዞታው በእጃቸው እንዴት እንደገባ ስላላረጋገጡ ተጠሪ ሁከት አልጠረችም መባሉ በሰበር መዝገብ ቁጥር 70801(በቅጽ 13 እንደታተመው) የተሰጠውን አስገዳጅ ውሳኔን የሚቃረን መሆኑን ፤ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ኑዛዜ ቤቱን የሚመለከት ሆኖ ሌሎችን ንብረቶች የኑዛዜ አውራሽ ለመሆኑ ማስረጃ ባልቀረበበት እና ተጠሪ ንብረቶቹን ለግል ጥቅማቸው ያዋሉ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የንብረቶቹን ግምት እንዲከፍሉ አለመወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት

በመሆኑ ለሰበር ቅሬታው ምክንያት የሖነው ውሳኔ ተሽሮ ሁከት እንዲወገድ እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡

በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 6/1 መሠረት ለሰበር ሰሚው ችሎቱ የተመራው የሰበር አቤቱታ በሰበር ሰሚ ችሎቱ ተመርምሮ የተጠሪ የኑዛዜ ወራሽነት በፍርድ ቤት ስለፀደቀ በአከራካሪው ቤት ላይ የተሻለ መብት አላቸው በሚል አመልካች ያቀረቡት ክስ ውድቅ የመሆኑን አግባብነት ለማጣራት ተብሎ ተጠሪ በሰጡት መልስ፡- አመልካች አከራካሪዎቹን ንብረቶች ከአመልካች በአደራ የተቀበሉ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ አለመቅረቡን ፤ ቤቱን የሚቆጣጠሩ እና ኪራይ ይቀበሉ የነበሩት ተጠሪ ስለነበሩ የግራ ቀኙ ጋብቻ ፀንቶ በነበረበት ወቅት አመልካች ቤቱን ይቆጣጠሩ እና ኪራዩንም ተቀብለው ለተጠሪ ይሰጡ የነበረ ቢሆንም በመካከላቸው የነበረው ጋብቻ ከፈረሰ በኋላ አመልካች ቤቱን ለማስተዳደርና ለመቆጣጠር ሲሞክሩ በቤቱ ላይ መብትና ጥቅም የላቸውም በማለት ተቃውሞ ያቀረቡ መሆኑን ፤ ለሁከት ክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት ሟች ወ/ሮ አልማዝ አየለ ለወ/ሮ ጌጠነሽ አየለ እና ለተጠሪ ስለተናዘዙ የሟች የኑዛዜ ወራሽነት ማስረጃ በመውሰድ ከአመልካች ጋር ከተለያዩ በኋላ ለክርክሩ ምክንያት ወደ ሖነው ቤት በመሄድ ተከራዮችን በማስወጣት ቤቱን ስለተረከብኩ የውርስ ሀብቱ ከአውሽ ወደ ወራሽ በመተላለፉ የተፈጠረ ሕገ-ወጥ ተግባር የለም፡፡ አመልካች የሟቿ ወ/ሮ አልማዝ አየለ ወራሽ ስላልሆኑ ከተጠሪ የተሻለ መብት እና ጥቅም ያላቸው መሆኑ ስላልተረጋገጠ ያቀረቡት የሁከት ይወገድልኝ ክርክር መሠረተ ቢስ መሆኑ ተረጋግጦ ውድቅ መሆኑ የሚነቀፍ ስላልሆነ ለሰበር ክርክሩ ምክንያት የሖነው ውሳኔ ፀንቶ ወጪ እና ክሳራ እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል።

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ፤ እኛም ለሰበር አቤቱታው መነሻ በሆነው ውሳኔ ላይ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ሲባል የተያዘውን ጭብጥ ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በሕግ ጥበቃ ከሚደረግላቸው የንብረት መብቶች ውስጥ በላይዞታነት የፍትሐ ብሔር ሕገ ቁጥር 1140 እና ተከታዮቹ ፤ በለሀብትነት የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1204 እና ተከታዮቹ ፤ በአላባ የመጠቀም መብት የፍትሐ ብሔር ሕገ ቁጥር 1349 እና ተከታዮቹ ተጠቃሾች

ናቸው፡፡ እያንዳንዱ የንብረት መብት ጥበቃ የራሱ ዓላማ አለው፡፡ በአንድ ነገር (thing) ላይ የተለያዩ የንብረት መብቶች ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች ሊቋቋም ስለሚችል ፣ እንደዚሁም በአንድ ዓይነት የንብረት መብት ብቻ ከአንድ ነገር ሊገኝ የሚገባውን አገልግሎት(ጥቅም) ማግኘት አዳጋች ሊሆን የሚችልባቸው ሁኔታዎችም ስላሉ በአንድ ነገር ላይ የተለያዩ በሕግ ጥበቃ የሚደረግላቸው መብቶች እንድኖሩ ምክንያት ሆኗል፡፡ ከንብረት መብቶች ውስጥ ከሁሉ የሰፋው ባለሀብትነት ቢሆንም ባለሀብትነት ብቻውን በነገሩ ሙሉ የመገልገል መብትን አያጎናጽፍም፡፡ ሌሎች ሰዎችን አግልሎ አንድን ነገር በራሱ ቁጥጥር ሥር አድርጎ የያዘ ሰው በነገሩ በአግባቡ መገልገል እንዲችል የሌሎች ሰዎች ጣልቃገብነት ፣ ረብሻ ፣ ሁከት ወ.ዘ.ተ ሊወገድለት ይግባል፡፡ የዚህ ዓይነቱ የሕግ ጥበቃ በሌለበት በያዙት ነገር ላይ የሌሎች ሰዎችን ጣልቀገብነት ፣ ረብሻ ፣ ሁከት ወ.ዘ.ተ ማስቆም ስለማይያቻል ሕይወት ውስብስብ መሆኑ አይቀሬ ነው፡፡

በፍትሐብሔር ሕጉ ቁጥር 1140 ድንጋጌ መሠረት ይዞታ አንድ ሰው አንድን ነገር በእጁ አድርጎ በእውነት የሚያዝበት ሆኖ ሲገኝ እንደሆነ ትርጉም ተሰጥቶታል፡፡ በእጁ አድርጎ በእውነት ማዘዝ(መቆጣጠር) በቀጥታ ወይንም ቀጥታ ባልሆነ መንገድ ሊሆን እንደሚችል የቁጥር 1141 ድንጋጌ ያመለክታል። በእውነት ማዘዝ ማለት ንብረቱን በእጁ አድርጎ መገኘት ብቻ ሳይሆን በንብረቱ ላይ በእውነት ማዘዝ እንዲችል የንብረት አያያዙ ያልተጭበረበረ እና በማንኛውም ሕገ ወጥ መንገድ ያልተገኘ መሆን እና የተሻለ የይዞታ መብት ያለው መሆኑን ያመለክታል፡፡ ባለይዞታ የሆነ ሰው ይዞታውን ለመንጠቅ ወይንም በይዞታው ላይ ሁከት ለማንሳት የሚደረገውን ተግባር በኃይል ለመከላከል ፣ በጉልበት የተወሰደበትን ነገር የማስመለስ ፣ ነጣቂውን የማስወጣት መብት ያለው መሆኑን የቁጥር 1148 (1) እና (2) ድንጋጌ ያመለክታል። የተወሰደው ነገር እንዲመለስለት ፣ የሁከት ተግባሩ እንዲወገድ እና የደረሰ ጉዳትም ካለም ካሳ መጠየቅ እንደሚችል ቁጥር 1149(1) ይደነግጋል፡፡ የሁከት ይወገድልኝ ክስ አቅራቢ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ነገር በቀጥታ ወይንም በጠባቂ ይዞታ ሥር መኖሩን ፣ የሁከት ድርጊት ፈፃሚው የኃይል ተግባር በመጠቀም በይዞታው ሥር ያለውን ንብረት እንዳይገለገልበት ጣልቃገብነት ፣ረብሻ ፣መሰናክል የፈጠረበት መሆኑን ወይም በሚስጥር ንብረቱን የወሰደበት መሆኑን በማንኛውም ለጉዳዩ አግባብነት ባለው ማስረጃ ከሁከት ድርጊት ፈፃሚው የተሸለ መብት ያለው መሆኑን ሚዛን በሚደፋ ማስረጃ ማስረዳት ይጠበቅበታል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በሁከት ተግባር ጉዳት ደርሶብኛል የሚል ተከራካሪ የንብረት ጉዳት የደረሰበት ስለመሆኑ የማስረዳት ኃላፊነት አለበት፡፡

በይዞታው ላይ የተፈጠረውን ሁከት ለማስወገድ በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1149 ድንጋጌ መሰረት የሚያቀርበው ክስ በፍ.ብ.ሕግ ቁጥር 1206 ባለሐብትነትን የማረጋገጥ (የመፋለም ክስ) የተለየ መሆኑን መገንዘብ ይገባል፡፡ የሁለቱ ክሶች ጭብጥ ፣ ጭብጡን ለማስረዳት የሚቀርቡ ማስረጃዎች ፣ እንዲሁም የክርክሩ አወሳሰን(dispute resolution) ልዩነት አላቸው፡፡ ስለሆነም አንድ ሰው በይዞታ መብቱ ላይ ሁከት የተፈጠረበት መሆኑን ጠቅሶ ሁከቱ እንዲወገድለት በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 1149/1 መሠረት ዳኝነት ከጠየቀ ማስረዳት የሚጠበቅበት ክርክር የተነሳበት ንብረት ባለሀብት መሆኑን ሳይሆን፤ባልተጭበረበረ ወይም ሕገወጥ ባልሆነ መንገድ ንብረቱን በእጅ አድርጎ በእውነት የሚያዝበት መሆኑን ነው፡፡ ከሳሽ አንድ ንብረት በአንድ ህጋዊ ተግባር ሳቢያ ወደ እጁ መግባቱን በመግለፅ በይዞታው ላይ ሁከት ተፈጥሮብኛል በሚል የሚያቀርበውን የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታ በእርግጥም ሁከት ተፈጥሯል አልተፈጠረም የሚል ጭብጥ በመያዝ ሊስተናገድ የሚገባ እንጂ ክርክር የተነሣበት ንብረት በከሳሹ እጅ እንዴት እንደገባ ወይም ወደ ከሳሹ እጅ ሊገባ የቻለበትን ህጋዊ ተግባር ለመመርመር የሚያበቃ ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍትሐ ብሔር ሕግ 1149 አተረጓጎንም በሚመለከት በመዝገብ ቁጥር 70801 ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ተከሳሹም ድርጊቱ በሕግ የተፈቀደ የሁከት ተግባር አለመሆኑን ወይንም ድርጊቱን ለመፈፀም መብት ያለው መሆኑን በማይታበል ማስረጃ በማስረዳት የቀረበበትን የሁከት ይወገድ ክስ መከላከል እንደሚችል ቁጥር 1149/3 ይደነግጋል።

በተያዘው ጉዳይ የአመልካች የክስ አቤቱታ ከወ/ሮ አልማዝ አየለ በአደራ ተቀብለው ለ7(ሰባት) ዓመታት  በእጃቸው አድርገው የሚያዙበትንና የኪራይ ገቢውን የሚጠቀሙበት ቤት እንዲጠብቁላቸው ያስቀመጡትን ሰዎች በማባረር እና ቤቱን ሰብሮ በመግባት ቤቱንና በቤቱ ውስጥ ያሉ ንብረቶችን በጉልበት በመያዝ እየተጠቀሙበት እንዳሉ በመግለጽ ተጠሪ ንብረቶች ላይ የፈጠሩት የሁከት ተግባር ተወግዶ ቤቱና እና ሌሎች ንበረቶችን ለቀው እንዲወጡ ፤ በሁከቱ ምክንያት ያጡት የኪራይ ጥቅም እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪም ለክስ አቤቱታው በሰጡት መልስ የቤቱ ባለቤት የነበሩት ከ1981 ዓ.ም ጀምሮ ያሳደጓቸው እናታቸው ሟች ወ/ሮ አልማዝ አየለ በ2004 ዓ.ም ህይወታቸው ስላላፈ በወራሽነታቸው በቤቱም ሆነ በቤቱ ውስጥ ያሉ ንብረቶች የማዘዝ መብት ስላላቸው ሲያዙበት የነበረ በይዞታቸው ሥር መኖሩን

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ገልፀው አመልካች ከተጠሪ ጋር በነበራቸው የትዳር ግንኙነት የፍቺ ውሳኔ እስከተሰጠበት ጊዜ ድረስ እንደቤተሰብ በቤቱ አብሮ ከመኖር ባለፈ ሕጋዊ በቤቱ የማዘዝ መብት ስላልነበራቸው አንድም ቀን በቤቱ አዘው እንደማያውቁ ተከራክረዋል፡፡ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ በአደራ የተረከቡት ቤት እና ንብረት ላይ የተፈጠረ የሁከት ድርጊት እንዲወገድላቸው እንጅ የመፋለም ክስ ባለመሆኑ ያላቸው መብት ወሰን ሊመረመር የሚገባው ከተጠየቀዉ ዳኝነት አንፃር ብቻ በመሆኑ አከራካሪው ቤት እና ንብረት የወ/ሮ አልማዝ አየለ መሆኑና እሳቸውም በህይወት እንደለሉ ስላላከራከረ በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 826/2 መሠረት የሚች የንብረት መብት ወደ ተጠሪ በውርስ መተላለፍ አለመተላለፉ በሁከት ይወገድልኝ ክስ በጭብጥነት ተይዞ የሚመረመር አይደለም፡፡ ከግራ ቀኙ የተሻለ መብት ያለው ማነው? የሚለውም መታየት ያለበት ከተጠየቀው የሁከት ይወገድልኝ ዳኝነት አንፃር እንጅ በአንድ ንብረት ላይ ሁለት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች የተለያየ የንብረት መብት ሊኖራቸው ስለሚችል ተጠሪ በፍትሐ ብሔር ሕጉ 1204 መሠረት ከሁሉ የሰፋ የንብረት መብት ያላቸው ቢሆን እንኳን አመልካች ባልተጭበረበረ ሕጋዊ በሆነ መንገድ በያዙት ንብረት ላይ ባላቸው መብት ልክ ተጠሪ ሁከት ፈጥሮባቸው ከሆነ በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 1149/3 መሠረት የሁከት ድርጊቱ እንዲቆም ፤ በድርጊቱ ጉዳት ድርሶ ከሆነም ካሳ የማግኘት መብት ያላቸው ሲሆን አከራካሪው ቤት በአመልካች ይዞታ ሥር ከነበረ እና እንደተጠሪ ክርክር በውርስ ተላልፎላቸው ከሆነ ንብረቱን መረከብ ያለባቸው በሕጉ በተቀመጠው አግባብ እንጅ በሁከት ድርጊት ሊሆን አይገባም፡፡ ስለሆነም አከራካሪውን ቤት እና ንብረት በእጁ አድርጎ በእውነት የሚያዝበት ማን እንደሆ ፤ የንብረት አያያዝ ባልተጭበረበረ መንገድ ያልተገኘ(በሕጋዊ መንገድ የያዘ ማን እንደሆነ ፤ የተሻለ የይዞታ መብት ያለው ማን እንደሆነ ሳይጣራ ተጠሪ የአከራካሪውን ቤት የኑዛዜ ወራሽ ስለሆኑ ከአመልካች የተሻለ መብት አላቸው በማለት የተሰጠው ውሳኔ የሰበር ሰሚ ችሎቱ በሰበር መዝገብ ቁጥር 70801 ላይ የተሰጠውን አስገዳጅ ውሳኔን ስለምጣረስ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2/4 ፤ (ለ)፤ እና (ሸ) መሠረት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

**ውሳኔ**

1. የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 06737 ግንቦት 2 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ብይንና እና ትዕዛዝ እንዲሁም የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 19719 የካቲት 20 ቀን

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና ትዕዛዝ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 9/1(ሀ) መሰረት **ተሽሯል**፡፡

2. የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍርድ የዘጋውን የመዝገብ ቁጥር 19719 በማንቀሳቀስ ሁከት መኖር አለመኖሩ ፣ የሁከት ድርጊት አለ ከተባለ በድርጊቱ የተቋረጠ የኪራይ ገቢ መኖር አለመኖሩን ፣ ለተቋረጠው የኪራይ ገቢ ተጠሪ ኃላፊነት ያለባቸው መሆን አለመሆኑን አጣርቶ ሕጋዊ ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ - ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 9/2 መሠረት መልሰንለታል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ውሳኔ አግኝቶ ስለተዘጋ ወደ መዝገብ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ/ጋ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ. 249399

ጥቅምት 04 ቀን 2017 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

ሰናይት አድነው

ሀፊዝ አባጀማል

**አመልካች**-፡- የጋሞ ዞን ትራንስፖርትና መንገድ ልማት መምሪያ -አ/ቤ ህግ አምሳሉ ብዙነህ

**ተጠሪ**፡- ሲና አነስተኛ ተቋራጭ ማህበር - ጠበቃ መብራቱ - ቀረቡ

ይህን መዝገብ ከመዝገብ ቁጥር 249388 ጋር በማጣመር መርምረን ተከታዩን ፍርዱ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

1. ይህ ጉዳይ የተጀመረው በጋሞ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበዉን ክስ መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡ ተጠሪ ባቀረበዉ ክስ ከአመልካች ጋር በተደረገዉ የግንባታ ዉል ስምምነት መሠረት ተጠሪ በጋሞ ዞን ሁለት ወረዳዎች ውስጥ አምስት የገጠር ቀበሌ ተደራሽ መንገዶችን እና አንድ ድልድይ ለመገንባት በገባዉ ግዴታ መሰረት ስራውን በመስራት ላይ እያለ ተጠሪ ከግንባታዉ ቦታ የለም በማለት አመልካች መጋቢት 02 ቀን 2013 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ውሉን ማቋረጡን ጠቅሶ አምስቱ የመንገድ ስራዎች እንዲሁም ድልድይ ስራ ተሰርቶ ያልተከፈለ ክፍያ፣ ውሉ ከህግ ዉጪ በመቋረጡ የታጣ ትርፍ 20%፣ የመያዥ ገንዘብ፣ ከቫት 50% ተመላሽ እና የሁሉ አቀፍ የመንገድና ድልድይ ስራዎች እንዲበረታቱ መስተዳድር ምክር ቤቱ ባስተላለፈው ውሳኔ መሰረት ተሰልቶ ለግንባታ ዕቃ እንዲሁም ለማሽነሪ ኪራይ የወጡ ወጪዎች በአጠቃላይ ብር 15,838,905.57 ከሕጋዊ ወለድ ጋር ይክፈለኝ በማለት ያቀረበዉን ዳኝነት መነሻ ያደረገ ነው፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

2. አመልካች በሰጠዉ መልስ ውሉ የተቋረጠው ተጠሪ በአራት ወራት ውስጥ ስራዉን አጠናቆ ለማስረከብ ውል ገብቶ ከሶስት ዓመት በላይ ማቆየቱን፣ በተደጋጋሚ የሚሰጡትን የእርምት ማስተካከያዎችን እና ትዕዛዞች ለመቀበል ተጠሪ ፈቃደኛ ካለመሆኑም በላይ ከስራ ተግባር ውጪ በፖለቲካ ውስጥ ገብቶ ሕዝብን የማወክ ተግባር ስለፈፀመ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ውሉ በህግ አግባብ መቋረጡን፤ የክልል መስተዳድር ምክር ቤት ያደረገዉ የቁርጥ ዋጋ ማስተካከያ ውል የተቋረጠበት ተቋራጭን የማይመለከት መሆኑን፤ የቫት ተመላሽ ክፍያ 50% የሚመለከተው ከህዳር 15 ቀን 2012 ዓ.ም በኃላ ስራ ላይ ያሉትን እንጂ ከዚያ በፊት የነበሩትን አለመሆኑን፤ 20% ክፍያ ለተሰራ ስራ እንጂ ላልተሰራ የሚከፈል አለመሆኑን፤ ተጠሪ ሰርቶ ያጠናቀቃቸውን ፕሮጀክቶች በተመለከተ በመያዣነት የተያዘው ገንዘብ የሚለቀቀው በስምምነቱ መሰረት ጊዜው ሲደርስ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ በበኩሉ ባቀረበዉ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ደግሞ ተጠሪ ከእያንዳንዱ ፕሮጀክት በእላፊ የወሰደው ገንዘብ እና ስራው ለሌላ ተቋራጭ በመሰጠቱ ተጨማሪ ወጪ በካሳ መልክ በድምሩ ብር 13,821,274.43 እንዲመልስ እንዲወሰን በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡
3. ጉዳዩ የቀረበለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ዉሉ የተቋረጠዉ በአመልካች ጥፋት ነዉ፤ ዉሉ በአመልካች ጥፋት የተቋረጠ ቢሆንም ተጠሪ የካሳ ጥያቄ ከተሰራ ስራ ክፍያ ጋር ተጠቃለዉ የሚቀርብ እንጂ በኪሳራ መልክ ለብቻዉ የማይጠየቅ መሆኑን፤ ለተሰራ ስራ ክፍያ በተሻሻላ የዋጋ ተመን ሊፈፀምልን ይገባል በማለት ተጠሪ ያቀረበዉ ዳኝነትም ተቀባይነት የለዉም፤ ከህዳር 15 ቀን 2012 ጀምሮ ለተጠሪ የሚከፈለው ክፍያ የቫት ክፍያ 50% ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፤ ሰላበር - ሾጮራ - ቆጎ መንገድ ፕሮጀክት ለመጨረሻ ጊዜ ተስተካክሎ በቀረበው ክፍያ መሰረት ለዚህ ፕሮጀክት የተከፈለው ቅድመ ክፍያ ያልተመለሰ ካለ ባልተመለሰው መጠን ተቀንሶ አመልካች እና የስር 2ኛ ተከሳሽ ባልተነጣጠለ ሃላፊነት እንዲከፍሉ፤ በተለያዩ ፕሮጀክቶች የተሰራን ስራ አስመልክቶ ለተጠሪ የተከፈሉ ክፍያዎችን ታስበዉ እና በገለልተኛ ባለሙያ ተጣርቶ ሊከፈል ይገባል፤ የዶሼ ፈትሌ መንገድ እና የጡማ ካሬ ድልድይ ፕሮጀክቶች ጊዚያዊ ርክክብ ሲደረግ ለግንባታዎች ደህንነት ዋስትና የተያዘው ገንዘብ በውላቸው መሰረት የመንገዱ ደህንነት ሲረጋገጥና የሚመለስበት ጊዜ ሲደርስ አመልካች እና የስር 2ኛ ተከሳሽ እንዲመልሱ በማለት ወስኗል፡፡
4. ግራ ቀኝ በየበኩላቸዉ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን፣ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱም ሁለቱን መዝገቦች በማጣመር ከመረመረ በኋላ በሁሉም ፕሮጀክት በዋስትና የተያዘን ገንዘብ በዚሁ መጠን ለዳኝነት የተከፈለ እና የጠበቃ አበል አመልካች ከስር 2ኛ ተከሳሽ ጋር በአንድነት እና በነጣላ እንዲከፍል፣ ሌሎች ወጪዎችን ዝርዝሩን ለስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ የማቅረብ መብት እንዳለዉ በመግለጽ ቀሪዎቹን የስር ፍ/ቤት ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡
5. ተጠሪ ይህንንም ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን፣ ሰበር ሰሚዉ ችሎትም በመ/ቁ 45187 ላይ ግራ ቀኙን በማከራከር ተጠሪ ውል ከመቋረጡ በፊት በሁሉም ሳይቶች ስራ ሰርቶ ያልተከፈለው ቀሪ ክፍያ እንዲከፈለው የተወሰነውን ገንዘብ በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በተሻሻለው አዲስ የዋጋ ስሌት መሰረት ከመጋቢት 02 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ገንዘቡን ከፍለው እስከሚያጠናቅቁ ድረስ ከሚታሰብ 9% ህጋዊ ወለድ ጋር በአንድነትና ባልተነጣጠለ ሃላፊነት ይክፈሉ፤ ተጠሪ ውሉ ባይቋረጥ ኖሮ በውላቸው መሰረት በእያንዳንዱ ሳይቶች ላይ ቀሪ ስራዎችን ሰርቶ ያገኝ የነበረው ትርፍ በቀሪው ስራ መጠን በባለሙያ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ተጣርቶ ሲያቀርብ አመልካች እና የስር 2ኛ ተከሳሽ ይክፈሉ፤ ተጠሪ በገባው የስራ ውል መሰረት በየሳይቶቹ ስራ ለመስራት ሲል ያቀረባቸውን ማሽነሪዎች በውሉ መቋረጥ ምክንያት ለባለንብረቶች ለመመለስ የሚያወጣቸውን የመጓጓዣ ወጪዎች አመልካች እና የስር 2ኛ ተከሳሽ ባልተነጣጠለ ሀላፊነት እንዲከፍሉ በማለት የስር ፍርድ ቤቶቹን ዉሳኔ አሻሽሎ የወሰነ ሲሆን፤ አመልካች በበኩሉ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ያቀረበዉን የሰበር አቤቱታ ችሎቱ በመዝገብ ቁጥር 46243 ላይ መርምሮ ተጠሪ በመ/ቁ 45187 ላይ ላቀረበዉ አቤቱታ አመልካች በሰጠዉ መልስ የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ሊፀና ይገባዋል በማለት መልስ መሰጠቱን፣ አመልካች ይህንን የምርመራ መዝገብ ከተጠሪ በኃላ ያስከፈተ ቢሆንም ተጠሪ ቀደም ብሎ ባስከፈተው የሰበር መዝገብ መልስ በሚሰጥበት ጊዜ መሰቀለኛ ይግባኝ አቤቱታ አለማቅረቡን፣ ሁለቱ መዛግብት ተጣምረዉ እንዲታዩ ችሎቱን ችሎቱን ሳያሳስብ መቅረቱንና አመልካች በዚህ መዝገብ ላይ ባቀረበዉ አቤቱታ የሚከራከረዉ ውሉ በተጠሪ ጥፋት መቋረጡንና ለዚህ የተጠየቀዉ ካሳ አለመከፈሉን በመጥቀስ ቢሆን በሌላ መዝገብ (45187 ላይ) ዉሳኔ ያረፈበት መሆኑን በአንድ ጉዳይ እርስ በእርሱ የሚጋጭ ዉሳኔ ሊሰጥ የማይገባ መሆኑን ጠቅሶ የሰበር አቤተታዉን ዉድቅ አድርጎታል።

6. ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም አመልካች በዚህ ሁኔታ በሁለቱም መዛግብት ላይ የተሰጠዉን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካች ሰኔ 16 ቀን 2015 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም አመልካች በውሉ መሠረት የ 30 ቀን ማስጠንቀቂያ በመስጠት ዉሉን ማቋረጥ ሲገባዉ የ15 ቀናት ማስጠንቀቂያ ብቻ ሰጥቶ አመልካች የዉል ጥሰት ፈጽሟል በማለት መወሰኑ፤ ውሉ እስከተቋረጠበት ድረስ ለተሰራ ስራ አዲስ በተሻሻለው የዋጋ መጠን መሰረት ከወለድ ጋር እንድንከፍል መወሰኑ፤ በውል ዋጋው ላይ መካካድ እና ትክክለኛውን መጠን በግልጽ እየነገርን ቢያንስ ለማስረጃነት የቀረበውን የውል ሰነድ መርምረው መወሰን ሲገባቸው ይህንን ማለፋቸው፤ ርክክብ የተፈፀመበት ቨርቫል እንደዚሁም ገለልተኛ አካል አጣርቶ እንዲያቀርብ ማዘዝ እየተቻለ ለክስ ፍጆታ ስልጣን በሌለው አማካሪ መሀንዲስ የተቀበናበረውን ሰነድ መነሻ አድርጎ ተጠሪ የጠየቀውን እንድንከፍል መወሰኑ መሰረታዊ የማስረጃ ምዘና መርህን የጣሰ ነዉ፤ ለውሉ ማቋረጥ ምክንያ የሆኑ የተጠሪ ጥፋት ሆኖ እያለ ወጪና ኪሳራ በአመልካች ላይ መወሰኑ፤ተጠሪ በቅድመ ክፍያ በኣላፊነት የወሰደው መመለስ ያለበት ገንዘብ አጣርቶ መወሰን ሲገባ ያለፈበት መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል የሚል ነው።

7. የሰበር አቤቱታዉ በሰበር ችሎቱ ተመርምሮ ያስቀርባል በመባሉም ተጠሪ መልሱን እንዲያቀርብ ተደርጎ ሚያዚያ 11 ቀን 2016 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ የስር ሁለተኛ ተከሳሽ (ዋናው ተዋዋይ) በችሎት ተከራካሪ ሆኖ ባለበት ሁኔታ ወካይ የማያነሳቸውን ነጥቦችን እያነሳ ተወካይ (አመልካች) የሚያደርገው መከራከሪያ ተቀባይነት የለውም፤ ከተጠሪ ጋር ውል የገባውና ዋናው የስራው ባለቤት ራሱ ተከራካሪ ሆኖ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ በመቃወም ለዚህ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/250253 ያቀረበው አቤቱታ ተዘግቷል። በስር ፍ/ቤቶች የተጠሪ ውል የተቋረጠው በውሉና በህጉ አግባብ አለመሆኑን በግራ ቀኞችን ማስረጃ ከመረጋገጡ በላይ ከተጠሪ ጋር የውል ግንኙነት የነበረው የስር ሁለተኛ ተከሳሽ ጭምር በደብዳቤ ያረጋገጠው እውነታ ነው። የስር ፍ/ቤቶች ተጠሪ እና በስር ሁለተኛ ተከሳሽ መካከል የነበረውን ውል አመልካች የውል ይሁን የህግ ድንጋጌዎችን ባልተከተለ ሁኔታ በማፍረሱ በውሉ መፍረስ ምክንያት በተጠሪ ላይ የደረሱትን የተለያዩትን ኪሳራ መክፈል ይገባል በማለት መወሰኑ አግባብ ነው፤ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የዋጋ ማሻሻያ መመሪያውን አውጥቶ ያጸደቀው የተጠሪ ውል ከመቋረጡ አስቀድሞ በቀን መጋቢት 01 ቀን 2013 ዓ.ም ሲሆን አመልካች የተጠሪን ውል አላግባብ ያቋረጡት ግን መመሪያው ወጥቶ ከጸደቀ በኋላ ማለትም በቀን 02/07/13 ዓ/ም በመሆነ ያልተከፈሉ ክፍያዎች ውላችን ከመቋረጡ አስቀድሞ በክልሉ ርእሰ መስተዳድር ጸድቆ በወጣው አድሱ ዋጋ ማሻሻያ መሰረት ተሰልቶ ሊከፈለው ይገባል በማለት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰጠው ውሳኔ ምንም የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት መሆኑን፤ ክፍያ እንዲፈጽም የክፍያ ሰርተፍከት ሳቀርብ ከአሰሪ የተከፈለውን ነገር ግን ክፍያውን ስመልስ የቀረውን ገንዘብ ተቀናንሶ የሚቀረውን ንጹህ ገንዘበን ብቻ መሆኑን በስር ፍ/ቤት ያቀረብኩት የእያንዳንዱ ሳይት ክፍያ ሰርትፍከት በራሱ ሰራተኛ በሆነው አማካሪ መሀንድስ የጸደቀው የሚያስረዳ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች ባቀረበዉ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

8. የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀውን ሲመስል ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታዉ መነሻ በሆነዉ ዉሳኔ ላይ የተፈጸመ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡

9. እንደሚታወቀዉ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80 (3/ሀ) ላይ በግልጽ እንደተመለከተዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉን ዉሳኔዎች በማረም ላይ የተገደበ ነዉ፡፡ መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት ነዉ? ወይም አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ መቼ ነዉ? የሚለዉን ጽንሰ ሃሳብ አስመልክቶ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ትርጓሜ ይሰጣል፡፡ በአዋጁ በትርጉም ክፍል አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለዉ አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን፣ ህግ ያላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉን ህግ የሚጠቅስ፣ ለክርክሩ አግባብነት ያለዉ ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለዉ ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፣ በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ዉድቅ በማድረግ የተወሰነ፣ በፍርድ አፈፃፀም ሂደት ከዋናዉ ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትዕዛዝ የተሰጠበት፣ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተወሰነ፣ የአስተዳደር አካል ወይም ተቋም ከህግ ዉጭ የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ በመቃረን የተወሰነ ሲሆን ነዉ፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በሚል የሰበር አቤቱታ ሲቀርብለት ለአቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ ጉዳይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ ከላይ በዝርዝር ከተመለከቱት ሁኔታዎች ዉስጥ ቢያንስ አንዱን ያሟላ ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 10 ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡

10. ከዚህ አንፃር የተያዘዉ ጉዳይ ስንመለከት፣ ከላይ እንደተገለጸዉ፣ አመልካች የስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ናቸዉ የሚላቸዉን ነጥቦች በዝርዝር ያቀረበ ሲሆን፤ የመጀመሪያዉ የቅሬታ ነጥቡ ዉሉ የተቋረጠዉ በአመልካች ጥፋት ነዉ በሚል የስር ፍርድ ቤቶች የደረሱበት ድምዳሜ እንዲሁም ካሳን አስመልክቶ የተሰጠ ዉሳኔን የሚመለከት ነዉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ ፍርድ ቤት አመልካች የዉል ጥሰት ፈጽሟል

በማለት ሲወስን መሠረት ያደረገዉ ዉሉን ማቋረጥ የፈለገ ወገን የ30 ቀን ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ ዉሉን ማቋረጥ እንደሚችል በግራ ቀኝ ዉል ላይ የተመለከተ መሆኑን፣ ዉሉ በአራት ወራት ጊዜ ዉስጥ መጠናቀቅ እንዳለበት በዉሉ የተገለጸ ቢሆንም ግራ ቀኝ በግልጽ ዉላቸዉን ሳያድሱ ነገር ግን ተጠሪ ለሚሰራቸዉ ስራዎች አመልካች ድጋፍ እያደረገ እንዲሁም ዉሉን በማቋረጥ ፕሮጀክቱን ለሌላ ተቋራጭ መስጠት አሠሪዉን ለተጨማሪ ወጪ ስለሚያስከትል ግራ ቀኝ በተቻለ መጠን ተቻችለዉ ስራዉን የያዘዉ ተጠሪ እንዲፈጽም ማድረግ የተሻለ ነዉ በሚል ስራዉ በተጠሪ እንዲቀጥል መደረጉ የዉሉን መፈጸሚያ ጊዜ እንዲራዘም አመልካች መስማማቱን እንደሚያሳይ፣ ከዚህም አልፎ ለዉሉ መቋረጥ አመልካች የጠቀሰዉ ምክንያት ዉሉ በተባለዉ ጊዜ ዉስጥ አለመጠናቀቁን ሳይሆን ተጠሪ በስራ ቦታዉ ላይ አለመገኘቱን ቢሆንም ተጠሪ በስራዉ ቦታ ላይ የነበረ መሆን አለመሆኑን ጨምሮ በአጠቃላይ የስራዉን ሂደት ተከታትሎ ሪፖርት የማድረግ ኃላፊነት ያለበት አማካሪ መሃንዲስ መሆን ሲገባዉ የወረዳዎችን ሪፖርት መሠረት በማድረግ ተጠሪ በስራ ቦታዉ የለም በሚል ዉሉን ማቋረጡ አግባብ አለመሆኑን በመጥቀስ ነዉ፡፡ ይህም የሚያሳየዉ ዉሉን ያላግባብ ያቋረጠዉ አመልካች ነዉ በሚል በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የጸናዉ ዉሳኔ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠዉን እና የግራ ቀኝን ዉል መሠረት ያደረገ ነዉ ከሚባል በስተቀር የሚነቀፍበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡

11. ዉሉ ያላግባብ ለመቋረጡ አመልካች ኃላፊነት አለበት በሚል መነሻ ዉሉ ባይቋረጥ ኖሮ ማግኘት ይችል የነበረዉን ተጠባቂ ትርፍ አመልካች እንዲከፍለዉ ተጠሪ ከጠየቀዉን ዳኝነት ጋር በተያያዘ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዉድቅ ያደረገዉ ተጠሪ በዚህ ረገድ ያቀረባቸዉ ክፍያዎች ከተሰራ ስራ ጋር ተጠቃለዉ የሚቀርቡ እንጂ እንደ ኪሳራ የሚጠየቁ አለመሆኑን በመጥቀስ ነዉ፡፡ በመሠረቱ በህግ አግባብ የተደረገ ዉል ዉሉን ባደረጉት ሰዎች መካከል መብትና ግዴታን የሚፈጥር የህግ ደረጃ የተሰጠዉ ተግባር በመሆኑ ተዋዋዮች በየበኩላቸዉ በዉሉ የሚጠበቅባቸዉን ግዴታ የመወጣት ኃላፊነት ያለባቸዉ መሆኑ እሙን ነዉ፡፡ ነገር ግን አንደኛዉ ወገን በዉሉ መሠረት የሚጠበቅበትን ግዴታ በተለያዩ ምክንያቶች ላይፈጽም የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ በዚህ ምክንያት ሌላኛዉ ተዋዋይ በዉሉ መሠረት ቢፈጸምለት ኖሮ ማግኘት ይችል የነበረዉን መብት/ጥቅም ሊያጣ ይችላል፤ በዉሉ መሠረት ይፈጸምልኛል በሚል ሌሎች ተጨማሪ ወጪዎችን ሊያወጣ የሚችልበት ሁኔታ ስለሚኖር ዉሉ ካልተፈጸመለት የዉሉን አፈፃፀም ታሳቢ በማድረግ ያወጣቸዉ ወጪዎች ከንቱ ስለሚሆኑ ለጉዳት ይዳረጋል፡፡ ይህ ሲሆን ዉል በተዋዋዮች መካከል ህግ ነዉ የሚለዉ የፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1731(1) ድንጋጌ ትርጉም የሚኖረዉ ዉሉ ባለመፈጸሙ ወይም የዉል ጥሰት በመፈጸሙ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት ተዋዋይ የሚካስበት ሥርዓት ሲኖር እና ተግባራዊ ሲደረግ ነዉ፡፡ የዉል አለመፈጸም ስለሚያስከትለዉ ዉጤት ወይም እንደዉሉ ያልተፈጸመለት ወገን ስለሚኖረዉ የህግ መፍትሔ (legal remedies) በፍትሐብሔር ህጋችን አንቀጽ 1771 እና ተከታዮቹ ላይ የተደነገገ ሲሆን፣ ከዚህ ዉስጥ አንዱ ለደረሰ ጉዳት ካሳ የመጠየቅ መብትን የሚመለከት ነዉ፡፡ በዉሉ መሠረት ያልተፈጸመለት ወገን ለደረሰበት የጉዳት ካሳ የመጠየቅ መብት ያለዉ ስለመሆኑ በህጉ አንቀጽ 1790(1) እና 1791(1) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ እንደዉሉ ያልተፈጸመለት ወይም የዉል መጣስ ተግባር የተፈጸመበት ወገን በጉዳት ካሳ ረገድ ከሚኖረዉ መብት ዉስጥ አንዱ ተጠባቂ ጥቅምን በካሳ መልክ የመጠየቅ መብት ስለመሆኑ በዉል ህግ ተቀባይነት ካገኙት መርሆዎች ዉስጥ አንዱ ነዉ፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

12. ከአስተዳደር መስሪያ ቤቶች ጋር ስለሚደረጉ ዉሎች ጋር በተያያዘ የፍትሐብሔር ህጉ ክፍል በአንቀጽ 3181(2) ላይ የተመለከተዉ ድንጋጌም ተጠባቂ ትርፍ በጉዳት ካሳ መልክ ሊከፈል እንደሚችል ያሳያል፡፡ በዙሪያ የተፃፉ ድርሳናትም ከግንባታ ዉል ጋር በተያያዘ ተጠባቂ ትርፍ በጉዳት ካሳ መልክ የሚከፈል በመሆኑ ላይ ጥያቄ የላቸዉም፡፡ ስለ ግንባታ ዉሎች በሚደነግገዉ የፍትሐብሔር ህጉ ክፍል በአንቀጽ 3036 ላይ የተመለከተዉ ድንጋጌም ይህንኑ የሚያሳይ ስለመሆኑ ከድንጋጌዉ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ ሁሉ መገንዘብ የሚቻለዉ፣ የግንባታ ዉልን ጨምሮ ማናቸዉም ዓይነት ዉል ቢሆን፣ እንደዉሉ ያልተፈጸለት ወገን በዉሉ አለመፈጸም ምክንያት ማግኘት ይችል የነበረዉን ጥቅም በካሳ መልክ የመጠየቅ መብት ያለዉ መሆኑን ነዉ፡፡ ስለሆነም ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ የጋሞ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለዉሉ መቋረጥ አመልካች ኃላፊነት አለበት በሚል ደምድሞ ነገር ግን የጉዳት ካሳ ከተሰራ ስራ ጋር ተጠቃሎ የሚታይ ነዉ በሚል ምክንያት ተጠሪ በዚህ ረገድ ያቀረበዉን ዳኝነት ዉድቅ ማድረጉ በርግጥም ስህተት በመሆኑ ይህንኑ በማረም በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

13. አመልካች ዉሉን ከህግ ዉጪ በማቋረጡ ምክንያት ለታጣ ትርፍ ለተጠሪ ሊከፈለዉ ይገባል ከተባለ መጠኑ ምን ያህል እንደሆነ ተጣርቶ የተወሰነ መሆን አለመሆኑ ቀጥሎ በተመለከተዉ መልኩ ተቃኝቷል፡፡ የጉዳት ካሳ የሚከፈለዉ ጉዳት መድረሱ ከተረጋገጠ ስለመሆኑ እሙን ነዉ፡፡ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1771(2)፣ 1790(1) እና 1791(1) ላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎችም ይህንኑ የሚያስገነዝቡ ናቸዉ፡፡ ስለሆነም ዉል ባለመፈጸሙ ምክንያት የጉዳት ካሳ በፍርድ ኃይል እንዲከፈለዉ የሚጠይቅ ተዋዋይ በርግጥም የደረሰበት ጉዳት መኖሩን የማስረዳት ሸክም አለበት፡፡ በርግጥ የካሳ ጥያቄዉ ዉሉ በመቋረጡ ምክንያት የታጣ ትርፍ ሲሆን የደረሰዉ ጉዳት መኖሩንና መጠኑንም አስመልክቶ በእርግጠኝነት ማስረዳት ባይቻልም ቢያንስ ጉዳት ስለመኖሩ ከሳሽ ምክንያታዊ በሆነ እርግጠኝነት እንዲያስረዳ ይጠበቃል፡፡ ይህም ሆኖ የጉዳት ካሳ መጠንን በመወሰን ረገድ ፍርድ ቤት ከፍተኛ ሚና ያለዉ ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1799 ላይ ከተመለከተዉ ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ አንቀጽ *"የሚከፈለዉ ኪሳራ የሚታሰበዉ አእምሮ ያለዉ ሰዉ ዉሉ ባለመፈጸሙ ይደርሳል ተብሎ በሚገመተዉ አስተያየት ልክ ነዉ"* ካለ በኋላ *"የዉሉ መሠረቶች ናቸዉ ተብለዉ የሚያዙት የዉሉን ዓይነት መመልከት ብቻ ሳይሆን የተዋዋዮችን የሞያ ስራ፣ ከዚህ በፊት የነበራቸዉን ግንኙነት፣ ባለዕዳዉ የሚያዉቃቸዉን ሁኔታዎችና ማንኛዎቹንም አጋጣሚ ሁኔታዎች ሁሉ…"* ከግምት ዉስጥ መግባት እንዳለባቸዉ ይደነግጋል፡፡ ለተጎጂዉ የሚከፈል የካሳ መጠን ከደረሰዉ ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ ሊሆን ይገባል የሚለዉን አጠቃላይ የካሳ መርህንም ልብ ይሏል፡፡ ስለሆነም ለከሳሽ የካሳ ጥያቄ መነሻ ሊሆን የሚችል ጉዳት መድረሱ ከተረጋገጠ የካሳዉን መጠን በመወሰን ረገድ ፍርድ ቤት የተለያዩ ሁኔታዎችን ግምት ዉስጥ በማስገባት በአግባቡ አመዛዝኖ ተገቢዉን የመወሰን ኃላፊነት አለበት፡፡

14. ከዚህ አኳያ የተያዘዉን ጉዳይ ስንመለከት፣ ተጠሪ ባቀረበዉ ክስ ሊከፈል የሚገባዉን የካሳ መጠን ያሰላዉ ለእያንዳንዱ ፕሮጀክት ከተቀመጠዉ የዉሉን ዋጋ 20% ትርፍ ሊገኝ ይችላል በሚል እሳቤ ስለመሆኑ የክሱ ይዘት ያሳያል፡፡ ይሁንና ለዚህ መነሻ ምክንያቱ ምን እንደሆነ አልተጠቀሰም፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ በዉሉ መሠረት በርካታ ስራዎችን ያከናወነ ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም ዉሉ በአመልካች ጥፋት በመቋረጡ ምክንያት ተጠሪ የሚያጣዉ ተጠባቂ ትርፍ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አይኖርም ለማለት አይቻልም፡፡ ይሁንና መጠኑ ምን ያህል ነዉ? የሚለዉ ነጥብ የተለያዩ ሁኔታዎችን ከግምት ዉስጥ በማስገባት አጣርቶ መወሰንን ይጠይቃል፡፡ በርግጥ ከግንባታ ዉል ጋር በተያያዘ ተጠባቂ ትርፍን ማስረዳት ቀላል ላይሆን ይችላል፡፡ ሆኖም ቢያንስ ተጠሪ በተቋራጭነት ስራ ሲሰራ የነበረዉ የመፈጸም ብቃት፣ ስራዉን ለማከናወን የሚያስፈልግ የሰዉ ኃይል ብዛት፣ ለሠራተኞች የሚከፈል የጉልበት ዋጋ፣ ግንባታ ሊሰራ በታሰበበት ወቅት የነበረዉ የግንባታ ዕቃዎች ዋጋ ሁኔታ፣ የኮንስትራክሽን ሥራዉን ለማስተዳደር ሊወጣ የሚችለዉን አስተዳደራዊ ወጪ፣ በተመሳሳይ ወቅት በተመሳሳይ ስራ ላይ የተሰማሩ ተቋራጮች ያገኙት ትርፍ በአማካይ እና መሰል ሁኔታዎችን መሠረት ባደረገ መልኩ ተጠሪ ስራዉ ቢጠናቀቅ ኖሮ ማግኘት ይችል የነበረዉን ተጠባቂ ትርፍ መገመት ይቻላል፡፡ ይሁንና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪ ወደ ስራዉ የገባዉ 20% ትርፍ እንደሚያገኝ ግምት ወስዶ ነዉ በሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰዉ ለተጠሪ የተሰጠዉ የዋጋ ተመን የተቋራጩን ትርፍ ጭምር እንደሚያካትት በዉሉ መመልከቱን በመጥቀስ ነዉ፡፡ ይሁንና ችሎቱ በዚህ ረገድ የደረሰበት ድምዳሜ ለተጠሪ ሊከፈለዉ የሚገባ የተጠባቂ ትርፍ መጠን 20% ነዉ ወደሚል አያመራም፡፡ ይልቁንም አመልካች ዉሉን ከህግ ዉጪ በማቋረጡ ምክንያት በተጠሪ ላይ ለደረሰዉ የተጠባቂ ትርፍ ማጣት ኪሳራ መጠኑን ከፍ ሲል የተመለከቱትን ሁኔታዎች ከግምት ዉስጥ በማስገባት አጣርቶ እና አመዛዝኖ መወሰን እንዲችል ጉዳዩን ማስረጃን መዝኖ ዉሳኔ ለመስጠት ስልጣን ላለዉ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መመለስ ነበረበት፡፡ በመሆኑም የተጠባቂ ትርፍ ኪሳራ አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢ ቢሆንም ከካሳዉ መጠን ጋር በተያያዘ የሰጠዉ ዉሳኔ ስህተት በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

15. ሁለተኛዉ የአመልካች የቅሬታ ነጥብ ለተሰራዉ ስራ ሊከፈል የሚገባዉ በተሻሻለዉ ዋጋ መሠረት ነዉ በሚል የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ነዉ የሚል ነዉ፡፡ ተጠሪ በዚህ ረገድ ያቀረበዉን ዳኝነት ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ ፍርድ ቤት ዉድቅ ያደረገዉ የደቡብ ክልል መስተዳደር ም/ቤት በቁጥር ደአ/ር/መ130/47 መጋቢት 01 ቀን 2013 ዓ.ም ያደረገዉ የዋጋ ማሻሻያ ዓላማ በዋጋ ማነስ ምክንያት ሁሉ አቀፍ የገጠር ተደራሽ መንገዶች እየተስተጓጎሉ የመልካም አስተዳደር ጥያቄ እየፈጠሩ ስለሆነ ፕሮጀክቶቹን እየሰሩ ባሉ ማህበራት እንዲጠናቀቁ ለማድረግ ስለመሆኑ በተለይም የክልሉ መስተዳደር ም/ቤት ለደቡብ ብ/ብ/ክልላዊ መንግስት ትራንስፖርት ቢሮ መጋቢት 01 ቀን 2013 ዓ.ም ከፃፈዉ ደብዳቤ መረዳቱንና በግራ ቀኛቸዉ መካከል የነበረዉ የግንባታ ዉል የተቋረጠዉ መጋቢት 02 ቀን 2013 ዓ.ም በመሆኑ የዋጋ ማሻሻያዉ ለፕሮጀክቱ መጠናቀቅ አስተዋጽዖ አይኖረዉም የሚል ምክንያት በመስጠት ነዉ፡፡ በአንፃሩ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከፍተኛዉ ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የሰጠዉን ዉሳኔ በመሻር ለተሰራ ስራ የሚከፈል ክፍያ በተሻሻለዉ ዋጋ መሠረት ሊሆን ይገባል በማለት ሲወስን የጠቀሰዉ መሠረታዊ ምክንያት የዋጋ ስሌት ማሻሻያዉ የጸደቀዉ በግራ ቀኝ መካከል የነበረዉ ዉል ከመቋረጡ በፊት መሆኑን ነዉ፡፡ በሌላ በኩል፣ በከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ዉሳኔ ሃተታ ላይ እንደተገለጸዉ፣ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የነበረዉ ዉል የዋጋ ማሻሻያ መመሪያዉ በጸደቀ በማግስቱ ሲሆን፣ የዋጋ ማሻሻያዉ ዓይነተኛ ዓላማ በዋጋ ማነስ ምክንያት ሁሉ አቀፍ የገጠር ተደራሽ መንገዶች እንዳይስተጓጎሉ ለማድረግ ነዉ፡፡ ስለሆነም የዋጋ ማሻሻያዉ ተፈፃሚነት የሚኖረዉ የዋጋ ማሻሻያ መመሪያ ስራ ላይ ከዋለ በኋላ በተቋራጩ ለሚሰራ ስራ እንጂ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ከማሻሻያዉ በፊት ለተሰራ ስራ አይደለም፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን መመሪያዉ በስራ ላይ የዋለበትን ቀን ዉሉ ከተቋረጠበት ቀን እንዲሁም ከመመሪያ ዓላማ አኳያ በማገናዘብ ለተሰራ ስራ ለተጠሪ ሊከፈል የሚገባዉ ክፍያ የዋጋ ማሻሻያዉን ሊያካትት አይገባም በሚል የሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢ ሆኖ ሳለ፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሉ የተቋረጠዉ መመሪያዉ ስራ ላይ ከዋለ በኋላ መሆኑን ብቻ በመጥቀስ አመልካች ለተጠሪ ክፍያዉን በተሻሻለዉ ዋጋ መሠረት ሊከፍል ይገባል በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢ ባለመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

16. ሌላዉ የአመልካች የቅሬታ ነጥብ ከተሰራ ስራ ጋር በተያያዘ የተሰጠን ዉሳኔ የሚመለከት ነዉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ፣ ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረዉ፣ በተለያዩ ፕሮጀክት የተሰሩ ስራዎች በገለልተኛ ባለሙያ ተጣርቶ ለእያንዳንዱ ፕሮጀክት የተከፈለዉ ቅድመ ክፍያ ለተጠሪ ተመልሶ ለቀረዉ ፕሮጀክት ከሚከፈለዉ ተቀንሶ ለተሰራ ስራ ለአመልካች ክፍያ ይፈጸም በማለት ሲሆን፣ በዚህ ሁኔታ የተሰጠ ዉሳኔ እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጸንቷል፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለዉ ይህ ዉሳኔ በአፈፃፀም ሂደት ግራ ቀኙን ለተጨማሪ ክርክር የሚጋብዝ እና ያላለቀለት ዉሳኔ መሆኑን ነዉ፡፡ በመሠረቱ የዳኝነት ስራ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት ዕዉቅና የተሰጣቸዉን የግልጽነት እና የተጠያቂነት መርሆዎችን ከግምት ዉስጥ ባስገባ መልኩ ሊከናወን እንደሚገባ የሚታወቅ ነዉ (አንቀጽ 12 ይመለከቷል)፡፡ የፍትሐብሔር ሥ/ሥርዓት ህጉ፣ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ዕዉቅና ከሚሰጣቸዉ መርሆዎች ዉስጥ አንዱ የግልጽነት እና የተጠያቂነት መርህ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጋችን ላይ ከተመለከቱት የተለያዩ ድንጋጌዎች የምንገዘበዉ ነዉ፡፡ የፍርድ/ዉሳኔ አፃፃፍ እና ይዘቱን በተመለከተ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ ከአንቀጽ 180-183 ላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎችም እነዚሁን መርሆዎች ታሳቢ በማድረግ የተቀረጹ ስለመሆኑ ከየድንጋጌዎቹ ይዘትና መንፈስ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የፍርድ አፃፃፍ ሥርዓት የዳኝነት ነፃነት እና ተጠያቂነት መርህ ከሚረጋገጡባቸዉ መንገዶች ዉስጥ አንዱ ስለመሆኑም የሚታወቅ ነዉ፡፡ በፍርድ ዉሳኔ ላይ ስለሚሰፍሩ ነገሮች በሚል ርዕስ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጋችን አንቀጽ 182(1) ላይ በተለይ ከተመለከተዉ ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለዉ፣ አንድ የፍርድ ዉሳኔ የተያዘዉን ጭብጥ፣ ጭብጡ እንዴት እንደተወሰነና የተወሰነበትን ምክንያት የያዘ መሆን እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ የዳኝነት ሥራ የመጨረሻ ግቡ ሊፈጸም የሚችል ዉሳኔ መስጠት ስመሆኑም እሙን ነዉ፡፡ ግልጽ ዉሳኔ አለመስጠት፣ ዉሳኔዉ ለአፈፃፀም አስቸጋሪ እንዲሆን ወይም ሳይፈጸም እንዲቀር ሊያደርግ የሚችል ከመሆኑም በላይ፣ ለአፈፃፀም የቀረበዉ ዉሳኔ ይዘት ግልጽ ባለመሆኑ ወይም አከራካሪ መሆኑን ተከትሎ በትርጉም ክፍተቱን ለመሙላት በሚደረግ ጥረት በዋናዉ ፍርድ የተረጋገጠ መብትና ግዴታ በአፈፃፀም እንዲለወጥ ወይም እንዲሻሻል የማድረግ ዉጤት ሊያስከትል የሚችል ሲሆን፣ ይህ መሆኑም የፍርድ ቤቶችን ዉሳኔ ተገማችነት እና ተፈፃሚነት ጥያቄ ዉስጥ እንዲገባ ምክንያት ይሆናል፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ሲሰጡ፣ የሚሰጡት ዉሳኔ ግልጽ እና ሊፈጸም የሚችል መሆን አለመሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸዉ፡፡ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 183 (1-መ) ላይ የተመለከተዉ ድንጋጌም ፍርድ ቤቶች በሚሰጡት ዉሳኔ ተከሳሽ ለከሳሽ የሚፈጽመዉን ግዴታ በግልጽ ማሳየት እንዳለባቸዉ የሚያስገድድ ነዉ፡፡

17. ከዚህ አንፃር የተያዘዉን ጉዳይ ስንመለከት፣ ለተሰራ ስራ ለተጠሪ ሊከፈል የሚገባዉን እና ለአመልካች ሊመለስ የሚገባዉ የገንዘብ መጠን በባለሙያ እንዲሰላ በሚል በጋሞ ዞን ከፍተኛ ፍርድ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ቤት ተሰጥቶ እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የጸናዉ የዉሳኔ ክፍል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

18. ሌላዉ የአመልካች ቅሬታ ለግንባታ ማሽነሪዎች ወጪን የሚመለከት ነዉ፡፡ ተጠሪ በዉሉ መሠረት ስራዉን አጠናቆ ለማስረከብ ሲባል ካስገባቸዉ ማሽኖች ጋር በተያያዘ የወጣዉን ወጪ አመልካች እንዲተካለት ዳኝነት የጠየቀ ሲሆን ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከግንባታዉ ጠቅላላ ወጪ ጋር ተጠቃሎ የሚታይ በመሆኑ ዳኝነት የሚጠየቅበት አይደለም በማለት ዉድቅ ያደረገ ሲሆን፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በበኩሉ ተጠሪ በየሳይቶቹ ስራ ለመስራት ሲል ያቀረባቸዉን ማሽነሪዎች በዉሉ መቋረጥ ምክንያት ለባለንብረቶቹ ለመመለስ የሚያወጣቸዉን የማጓጓዣ ወጪዎች አመልካች የመክፈል ኃላፊነት እንዳለበት በመወሰን ይህን አስመልክቶ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ የሰጠዉን ዉሳኔ ሽሯል፡፡ ይሁንና ተጠሪ ዉሉ ከመቋረጡ በፊት የተሰሩ ስራዎች በርካታ መሆናቸዉ እና የማሽነሪዎች የትራንስፖርት ወጪ ለመክፈል እንደማይገደድ አመልካች ከሚያነሳቸዉ ክርክሮች አንፃር እንዲሁም ተጠሪ በስራዉ ምክንያት ወደ ሳይቶቹ ያስገቧቸዉ ማሽነሪዎች ዓይነት እንዲሁም ለባለንብረቶቹ ለመመለስ ለትራንስፖርት ወጪ መዉጣት አለመዉጣቱ በጭብጥነት ተይዞ መጣራት የሚገባዉ ነዉ፡፡ ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በዚህ ረገድ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ዉሳኔ ሽሮ ተጣርቶ እንዲወሰን መወሰን ሲገባዉ ይህን ሳያደርግ በደፈናዉ የማጓጓዣ ወጪዎችን አመልካች እና የስር 2ኛ ተከሳሽ ባልተነጣጠለ ኃላፊነት እንዲከፍሉ በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ ፍርድ ቤቶች የግራ ቀኙን ክርክር መሠረት ያደረገ የህግ እና የፍሬ ነገር ጭብጥ በመያዝ ክርክሮች በተገቢዉ ሁኔታ እንዲነጥሩ በማድረግ ፍትሐዊ ዉሳኔ የመስጠት ኃላፊነት እንዳለባቸዉ በፍት/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 246(1) እና 247(1) ላይ ከተመለከተዉ ድንጋጌ እንዲሁም ከላይ በተራ ቁጥር 16 ላይ ካነሳነዉ ሀተታ አንፃር ሲታይ መሠረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ መቃናት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ዉሳኔ**

1. የጋሞ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 42051 ላይ ሐምሌ 29 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት፣ የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 41368 ላይ ጥር 05 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 45187 ላይ ሚያዝያ 13 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት እንዲሁም በመ/ቁጥር 46243 ላይ ሰኔ 08 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጡት ዉሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1) መሠረት ተሻሽሏል፡፡

2. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 45187 ላይ ለተሰራ ስራ አመልካች ክፍያዉን በተሻሻለዉ ዋጋ መሠረት መክፈል አለበት በሚል የተሰጠ ዉሳኔ ክፍል ተሽሯል፤ በዚህ ረገድ ከፍተኛዉ ፍርድ ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ ጸንቷል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

3. አመልካች ለተጠሪ ተጠባቂ ትርፍ የመክፈል ኃላፊነት እንዳለበት በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ ተገቢ ሆኖ ነገር ግን አመልካች በእያንዳንዱ ሳይቶች ላይ ቀሪ ሥራዎችን ሠርቶ ያገኝ የነበረዉ ትርፍ በቀሪዉ ሥራ መጠን በባለሙያ ተሰልቶ ሲቀርብ ተጠሪዎች ይክፈሉ በሚል የተሰጠ የዉሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡

4. ለተሰራ ስራ ያልተከፈለዉ ሂሳብ እንዲከፈል በክልሉ በየደረጃዉ ያሉ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ ተገቢ ሆኖ ነገር ሂሳቡ በባለሙያ እንዲጣራ መባሉ ዉሳኔዉን የተሟላ የማያደርግና ለአፈፃፀም አስቸጋሪ ሚያደርግ በመሆኑ በዚሁ ልክ ተሻሽሎ ተወስኗል፡፡

5. ከማሽነሪዎች ወጪ ጋር በተያያዘ የክልሉ በየደረጃዉ ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠ ዉሳኔ ዉሳኔ ተሽሯል፡፡

6. የጋሞ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተዘግቶ የነበረዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ፡-

   6.1. ተጠሪ በተቋራጭነት ስራ ሲሰራ የነበረዉ የመፈጸም ብቃት፣ ስራዉን ለማከናወን የሚያስፈልግ የሰዉ ኃይል ብዛት፣ ለሠራተኞች የሚከፈል የጉልበት ዋጋ፣ ግንባታ ሊሰራ በታሰበበት ወቅት የነበረዉ የግንባታ ዕቃዎች ዋጋ ሁኔታ፣ የኮንስትራክሽን ሥራዉን ለማስተዳደር ሊወጣ የሚችለዉን አስተዳደራዊ ወጪ፣ በተመሳሳይ ወቅት በተመሳሳይ ስራ ላይ የተሰማሩ ተቋራጮች ያገኙት ትርፍ በአማካይ እና መሰል ሁኔታዎችን መሠረት በማድረግ የግራ ቀኝን ክርክር እና ማስረጃ እንዲሁም እንዳስፈላጊነቱ ተጨማሪ ማስረጃዎችን በማስቀረብ ተገቢዉን ማጣራት በማድረግ ዉሉ በመቋረጡ ምክንያት **ባልተሰራ ስራ ልክ** ተጠሪ ማግኘት ይችል የነበረዉን ተጠባቂ ትርፍ በማጣቱ የደረሰበትን የጉዳት ካሳ መጠን እንዲወስን፤

   6.2. ዉሉ ከመቋረጡ በፊት በእያንዳንዱ ፕሮጀክት የተሰራ ስራ መጠን እና ዋጋ፣ ለተሰራ ስራ የተከፈለ ክፍያ፣ ከተጠሪ ለአመልካች መመለስ የሚገባ ገንዘብ እና ከስራዉ ጋር በተያያዘ ሌሎች ወጪዎች ሁሉ በባለሙያ እንዲጣሩ በማድረግ ለተሰራ ስራ ለተጠሪ የሚከፈለዉን የገንዘብ መጠን ለይቶ እንዲወስን፤

   6.3. ተጠሪ በስራ ቦታ ካስገባቸዉ ማሽነሪዎች ጋር በተያያዘ የወጣዉን ወጪ አመልካች በካሳ መልክ የመተካት ኃላፊነት ያለበት መሆን አለመሆኑን እና የመክፈል ኃላፊነት አለበት የሚባል ከሆነም መጠኑ ምን ያህል እንደሆነ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ማስረጃ ጋር በማገናዘብ መርምሮ ተገቢዉን ዉሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(2) መሠረት ተመልሶለታል፡፡

7. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**ትዕዛዝ**

በዚህ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 249388 ላይ በመታየት ላይ ያለ ጉዳይ በዚህ መዝገብ እልባት አግኝቷል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 249487

ጥቅምት 7 ቀን 2017ዓ.ም

ዳኞች፡ ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

ሠናይት አድነው

ሀፊዝ አባጆማል

አመልካች - ወ/ሮ ሀይማኖት ገ/መስቀል ቀረበ

ተጠሪዎች፦ 1. ወ/ሮ እናኒ ሰይ ጠበቃ ማርታ አሰፋ

2. አቶ ፍስሐ ግርማ
3. አቶ ወንድሙ አበበ
4. አቶ ፍቅረዮሐንስ ለማ
5. ወ/ሮ ነቢሃ አብድልቃድር

(2–5) አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡

## ፍርድ

ይህ ክርክር የተጀመረው በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁን 1ኛ ተጠሪ ከሳሽ የአሁን ከ2-5 ያሉ ተጠሪዎች ተከሳሽ አመልካች ጣልቃ ገብ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለው የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 221271 መጋቢት 20 ቀን 2015 ዓ/ም በዋለው ችሎት የፌደራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በመሻር የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልካች ሰኔ 20ቀን 2015ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ 1ኛ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ሚያዝያ 18 ቀን 2001ዓ.ም ጋብቻ ፈጽመን 2 ልጆች ወልደን ንብረት አፍርተን ስንኖር ከወሊድ ጋር በተያያዘ ባጋጠመኝ ህመም የተለያየ ጸበል እና ህክምና ስከታተል እኔ በላወቅኩበት ሁኔታ 2ኛ ተጠሪ የሆነው ባለቤቴ በጋራ ያፈራነውን እና የጋራ ንብረታችን የሆነ አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 በካርታ ቁጥር 01262 በ2ኛ ተጠሪ ስም የተመዘገበ ቤት ታህሳስ 13 ቀን 2010ዓ.ም በተደረገ የመንደር ውል ለ3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች በሽያጭ ያስተላለፈ ስለሆነ 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎችም 2ኛ ተጠሪ ባለቤቴ ባለትዳር መሆኑን እያወቁ ከቅን ልቦና ውጪ የፈጸሙት ውል ስለሆነ በተሻሻለው የፌደራል የቤተሰብ አዋጅ ቁጥር 212/1992 አንቀጽ 68 እና 69 መሰረት እና ውሉም የመንደር ውል ስለሆነ እንዲፈርስ እና ወጪ እና ኪሳራ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

2ኛ ተጠሪ ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት የታየ ሲሆን 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርበዋል የአሁን 4ኛ ተጠሪም እኔ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር የፈጸምኩት የሽያጭ ውል ስለሌለ 1ኛ ተጠሪ በኔ ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት የላቸውም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን የአሁን አመልካችም ባቀረቡት የጣልቃ ገብ ክርክር 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ካቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የፍሬነገር ክርክር ጋር ተመሳሳይ ክርክር አቅርበዋል፡፡

ለዚህ የሰበር ችሎት አቤቱታ መነሻ የሆነው 1ኛ ተጠሪ  እኔ ሳላውቅ ባለቤቴ የሆነው 2ኛ ተጠሪ ከ3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ጋር የፈጸሙት የቤት ሽያጭ ውል ይፍረስልኝ በማለት ባቀረቡት ክስ ላይ 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች እና የአሁን አመልካች ይርጋን አስመልክቶ ያቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ የተሰጠ ውሳኔን መሰረት ያደረገ ሲሆን 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች እና የአሁን አመልካች ያቀረቡት መቃወሚያ 1ኛ ተጠሪ ውሉ ጥቅምት 20 ቀን 2010ዓ.ም አስቀድሞ በመንደር ሲደረግ ጀምሮ ያውቃሉ በሰነዶች ማረጋገጫ እና ምዝገባ ጽህፈት ቤት የተደረገው ታህሳስ 17 ቀን 2010ዓ.ም ነው ክስ ያቀረቡት የሽያጭ ውል መኖሩን ካወቁ 1አመት በኋላ ነው ስለሆነም በተሻሻለው የፌደራሉ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 212/1992 አንቀጽ 69 መሰረት ውሉ መኖሩን ካወቁ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ ማቅረብ ሲገባቸው ያላቀረቡ ስለሆነ ክርክራቸው በይርጋ ይታገዳል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ጉዳዩ የቀረበለት የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግራቀኙን አከራክሮ ማስረጃ ሰምቶ 1ኛተጠሪ ቤቱ መሸጡን በወቅቱ ያውቁ እንደነበር በበለጠ ተረጋግጧል፤ ውሉ ሲደረግ ታምሜ ጸበል ነበርኩ በማለት ያቀረቡት ማስረጃም ውሉ ከተደረገ ከአመት በኋላ ያለውን ጊዜ የሚመለከት በመሆኑ ከዚህ አንጻርም ያቀረቡት መከራከሪያ ተቀባይነት የለውም በአጠቃላይ 1ኛ ተጠሪ ውሉ ጥቅምት ወር 2010ዓ.ም ሲደረግ ጀምሮ ያውቁ የነበረ መሆኑ የተረጋገጠ እና ካወቁበት ጊዜ ጀምሮ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ ማቅረብ ሲገባቸው የ6 ወር ጊዜው ካለፈ በኋላ ሚያዝያ 4 ቀን 2011 ዓ.ም ያቀረቡት ክስ በተሻሻለው የፌደራሉ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 212/1992 አንቀጽ 69 (2) እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 244(2)ሠ መሰረት በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡

1ኛ ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ ቅሬታ ያቀረቡ ሲሆን ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ 1ኛ ተጠሪ በስር ክሳቸው 2ኛ ተጠሪ የሆኑት ባለቤታቸው ከ3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ጋር እኔ ሳላውቅ የፈጸሙት የቤት ሽያጭ ውል መኖሩን ያወቅኩት እኔ ከጸበል ከተመለስኩ በኋላ ነው ከማለት በስተቀር መቼ እንዳወቁ ቀኑን ሳይገልጹ ክስ ያቀረቡ ሲሆን የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በዚህ ክስ መነሻነት ግራ ቀኙን አከራክሮ የ1ኛ ተጠሪ ክስ በ6 ወር ይርጋ ይቋረጣል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ሆኖም ግን 1ኛ ተጠሪ ለዚህ ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ ቅሬታቸውን ሲያቀርቡ ከጸበል ሲመለሱ ጉዳዩን ያወቁት የካቲት 17 ቀን 2011ዓ.ም ነው በማለት ከገለጹት ቅሬታ ጋር ሲታይ ምንም እንኳን ከስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ማረጋገጥ እንደሚቻለው 1ኛ ተጠሪ ክስ ያቀረቡት ነሀሴ 14 ቀን 2012ዓ.ም ቢሆንም የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት 1ኛ ተጠሪ ክስ ያቀረቡበት ቀን ሚያዝያ 4 ቀን 2011ዓ.ም ነው በማለት ከመደምደሙ ጋር ተያይዞ የቀረበ የይግባኝ ቅሬታ የሌለ ስለሆነ ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚሰጥ የተለየ ውሳኔ የለም በማለት ደምድሞ ሆኖም 1ኛ ተጠሪ እሳቸው ፍቃዳቸውን ያልሰጡበት ውል መደረጉን ያወቁበትን ቀን ገልጸው ክስ ማቅረብ ሲገባቸው ያላቀረቡ ስለሆነ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት 1ኛ ተጠሪ በክሳቸው ላይ ፍቃዳቸውን ያልሰጡበት ውል መደረጉን ያወቁበትን ቀን ገልጸው ክሳቸውን አሻሽለው እንዲያቀርቡ ማድረግ ሲገባው ጉድለት ያለበትን ክስ ተቀብሎ ክሱን በመስማት ክርክሩ በይርጋ ይታገዳል በማለት ብይን መስጠቱ ስነ ስረአታዊ አይደለም በማለት ሽሮ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ በፍ/ብ/ስ/ስ/ ህግ ቁጥር 91 መሰረት ክሱ ተሻሽሎ እንዲቀርብለት በማዘዝ እንደገና ጉዳዩን አጣርቶ እንዲወስን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 341(1) መሰረት በመመለስ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የሰበር አቤቱታው ለዚህ ችሎት የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ሲሆን አመልካች ሰኔ 20 ቀን ቀን 2015 ዓ/ም በተፃፈ ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይዘት በአጭሩ በስር የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራ ቀኛችን በተከራከርንበት ጉዳይ አመልካች እና የአሁን 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ባቀረብነው የይርጋ መቃወሚያ መነሻነት ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኛችንን ክርክር እና ማስረጃ ሰምቶ የአሁን 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ በይርጋ ይታገዳል በማለት ብይን የሰጠ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ ባቀረቡት የይግባኝ ቅሬታ መነሻነት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከደረሰበት መደምደሚያ ጋር የማይገናኝ ለጉዳዩም አግባብነት የሌለው ምክንያት በመፍጠር የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ብይን በመሻር እንደገና ተጣርቶ እንዲወሰን ወደ ስር ፍርድ ቤት በመመለስ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊሻር ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካችም አቤቱታ ተመርምሮ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁን 1ኛ ተጠሪ ፍቃዳቸውን ያልሰጡበት ውል መደረጉን ውሉ ሲደረግ ጥቅምት 2010ዓ.ም ጀምሮ ያውቁ እንደነበር በማስረጃ የተረጋገጠ ፍሬነገር መሆኑን ድምዳሜ ላይ ከመድረሱ ጋር ተያይዞ 1ኛ ተጠሪ ከጸበል ተመልሰው ፍቃዳቸውን ሳይሰጡ የተደረገ ውል መኖሩን ያወቁበትን ቀን ገልጸው ክሳቸውን አሻሽለው እንዲያቀርቡ ተደርጎ ተጣርቶ እንዲወሰን ወደ ስር ከፍተኛ ፍርደ ቤት በመመለስ የሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 91 ድንጋጌ አንጻር ለመመርመር ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ በመደረጉ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሠረት 1ኛ ተጠሪ መጋቢት 16 ቀን 2016 ዓ/ም የተፃፈ መልስ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም በአጭሩ በክስ ማመልከቻዬ ላይ ሽያጩን ያወቅኩበት ቀን ያልተገለጸ ስለሆነ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ክሱ በዚህ አግባብ ተሻሽሎ ቀርቦ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ወደ ስር ፍርድ ቤት በመመለስ የሰጠው ውሳኔ የተፈጸመበት የህግ ስህተት ባለመኖሩ ጸንቶ ይወሰንልኝ በማለት ሲከራከሩ 2ኛ ተጠሪ ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ በመታዘዙ ያቀረቡት መልስ የሌለ ሲሆን 3ኛ፤ 4ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች በበኩላቸው 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች በአንድ ላይ 5ኛ ተጠሪ በግላቸው ያካቲት 22 ቀን 2016ዓ.ም በተጻፈ ያቀረቡት መልስ በአጭሩ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ብይን ሊጸና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም ግንቦት 9 ቀን 2016ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና የክርክሩ ይዘት በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ እና ማስቀረቢያ ጭብጡን መሰረት በማድረግ አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

እንደመረመርነውም 1ኛ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ጋብቻ ፈጽመን ልጆች ወልደን ንብረት አፍርተን ስንኖር ከወሊድ ጋር በተያያዘ ባጋጠመኝ ህመም የተለያየ ጸበል እና ህክምና ስከታተል እኔ በላወቅኩበት ሁኔታ 2ኛ ተጠሪ የሆነው ባለቤቴ በጋራ ያፈራነውን እና የጋራ ንብረታችን የሆነ ቤት ታህሳስ 13 ቀን 2010ዓ.ም በተደረገ የመንደር ውል ለ3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች በሽያጭ ያስተላለፈ ስለሆነ 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎችም 2ኛ ተጠሪ ባለቤቴ ባለትዳር መሆኑን እያወቁ ከቅን ልቦና ውጪ የፈጸሙት ውል ስለሆነ በተሻሻለው የፌደራል የቤተሰብ አዋጅ ቁጥር 212/1992 አንቀጽ 68 እና 69 መሰረት እና ውሉም የመንደር ውል ስለሆነ እንዲፈርስ እና ወጪ እና ኪሳራ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች 1ኛ ተጠሪ ውሉ ሲደረግ ጀምሮ ያውቁ ስለነበር ካወቁበት ጊዜ ጀምሮ በ6ወር ወይም በጠቅላላው በ2 አመት ጊዜ ውስጥ ክሱን ያላቀረቡ ስለሆነ ክርክሩ በይርጋ ይታገዳል በማለት ያቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመቀበል ክርከሩ በይርጋ ይታገዳል በማለት ሲወስን ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት 1ኛ ተጠሪ እሳቸው ፍቃዳቸውን ያልሰጡበት ውል መደረጉን ያወቁበትን ቀን ገልጸው ክስ ማቅረብ ሲገባቸው ያላቀረቡ ስለሆነ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት 1ኛ ተጠሪ በክሳቸው ላይ ፍቃዳቸውን ያልሰጡበት ውል መደረጉን ያወቁበትን ቀን ገልጸው ክሳቸውን አሻሽለው እንዲያቀርቡ ማድረግ ሲገባው ጉድለት ያለበትን ክስ ተቀብሎ ክሱን በመስማት ክርክሩ በይርጋ ይታገዳል በማለት ብይን መስጠቱ ስነ ስረአታዊ አይደለም በማለት ሽሮ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ በፍ/ብ/ስ/ስ/ ህግ ቁጥር 91 መሰረት ክሱ ተሻሽሎ እንዲቀርብለት በማዘዝ እንደገና ጉዳዩን አጣርቶ እንዲወስን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 341(1) መሰረት በመመለስ ውሳኔ መስጠቱን ከስር ፍርድ ቤቶች የውሳኔ ግልባጮች መረዳት የሚቻል ጉዳይ ነው፡፡

የክስ መሻሻልን አስመልክቶ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 91(1) ላይ ከተመለከተዉ ድንጋጌ መገንዘብ እንደሚቻለዉ በተከራካሪ ወገኖች በአንደኛው ጠያቂነት ወይም በፍርድ ቤቱ በእራሱ አነሳሽነት ክስ ተሻሽሎ እንዲቀርብ ሊደረግ የሚችልበት ሁኔታ ሲሆን፣ ፍርድ ቤቱ አቤቱታ ተሻሽሎ እንዲቀርብ የሚፈቅደዉ ወይም ትዕዛዝ የሚሰጠዉ የአቤቱታዉ መሻሻል ነገሩን ይበልጥ የሚያብራራ ወይም ትክክለኛ ፍትሕን ለመስጠት የሚረዳ ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ የድንጋጌዉ ይዘት ያሳያል፡፡ በተጨማሪም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 232588 እና በሌሎችም ተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በተያዘዉ ጉዳይ የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 91 መሠረት ለክስ ማሻሻያ ምክንያት ያደረገው 1ኛ ተጠሪ በክሳቸዉ እሳቸው ፍቃዳቸውን ያልሰጡበት ውል መደረጉን ያወቁበትን ቀን ገልጸው ክስ ማቅረብ ሲገባቸው አካተዉ ያላቀረቡ ስለሆነ ያወቁበትን ቀን ገልጸው ለማቅረብ ሲባል ክሱ መሻሻል አለበት በማለት ድምዳሜ ላይ ደርሶ ነው፡፡

እንደሚታወቀዉ ከፍርድ ቤት አንድን ዳኝነት ለመጠየቅ የሚቀርብ አቤቱታ ግልጽ እና የአቤቱታዉን ዓይነት መሠረት ባደረገ መልኩ ለጉዳዩ አግባብነት ባለዉ ድንጋጌ ላይ የተመለከቱትን ሁኔታዎች አሟልቶ መቅረብ ያለበት ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 80(2)፣ 213(1)፣ 216(1) እና 222(1)ረ ድንጋጌዎች የተመለከተ ከመሆኑም በተጨማሪም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 91329 እና በሌሎችም ተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

ዓላማዉም ተከራካሪ ወገኖች የክርክሩን ምክንያትና የተጠየቀዉን ዳኝነት አዉቀዉ ተገቢዉን ክርክር ማቅረብ እንዲችሉ እና ፍርድ ቤቱም ክርክሩን የግራ ቀኙን የመከራከር መብት ያገናዘበ እና ሚዛናዊ በሆነ ሁኔታ በመምራት በጉዳዩ ላይ ፍትሐዊ ዉሳኔ እንዲሰጥ ማስቻል ነዉ፡፡ አቤቱታ እንዲሻሻል በፍርድ ቤት የሚፈቀድበት (የሚታዘዝበት) ምክንያትም አቤቱታ ግልጽ ሆኖ ወይም ተብራርቶ መቅረቡ ብሎም ከሳሽ (ተከሳሽ) መጀመሪያ ክሱን (መልሱን) ሲያቀርብ በስህተት ወይም በሌላ ምክንያት ሳያካትት የቀረዉን ፍሬ ነገር አካቶ እንዲያቀርብ ዕድል በመስጠት ክርክሩን ሚዛናዊ በሆነ ሁኔታ በመምራት የግራ ቀኙን ትክክለኛ ክርክር ያገናዘበ ፍትሐዊ ዉሳኔ ለመስጠት እንደሆነ ይታመናል፡፡

በተያዘው ጉዳይ 1ኛ ተጠሪ በመጀመሪያው ክሣቸው የጠየቁት ካለ እኔ እውቅና እና ፍቃድ ውጪ 2ኛ ተጠሪ የሆነው ባለቤቴ ከ3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ጋር የፈጸመው የቤት ሽያጭ ውል ይፍረስልኝ የሚል ሲሆን በክሳቸው ላይ በወቅቱ እኔ ጳበል ሄጄ ስለነበር ቤቱ መሸጡን ያወቅኩት ከጸበል ስመለስ ነው ከማለት በስተቀር በትክክል ያወቁበትን ቀን ያልገለጹ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያሳያል፡፡ አመልካች ቤቱ መሸጡን ያወቅኩት ከጸበል ስመለስ ነው በማለት የገለጹበት ምክንያት በወቅቱ ውሉ እንዲፈርስ ያልጠየቁት ባለመኖራቸው እና በዚህም ምክንያት ውል መደረጉን ያለማወቃቸውን ለመግለጽ እና ከዚህ ጋር ተያይዞ ሊነሳ የሚችል የይርጋ መቃወሚያን መልስ ለመስጠት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ከጸበል መቼ እንደተመለሱ እና እሳቸው ያልፈቀዱት የሽያጭ ውል መደረጉን ያወቁበትን ቀን ገልጸው ክስ ሊያቀርቡ ይገባል፡፡

ይህ እንዲሆን ለአንድ የክስ አቤቱታ አቅራቢ ከላይ የተመለከተቱ የህግ ድንጋጌዎች እና የሰበር ሰሚ ችሎት አስገዳጅ የህግ ትርጉም ያስገድደዋል፡፡ ስለሆነም በዚህ አግባብ ተሟልቶ ያልቀረበ የክስ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ. ቁጥር 91 መሰረት ለክስ ማሻሻያ ምክንያት ማድረግ ተከራካሪዎች ያላሰቡትን እና ያልፈለጉትን ክርክር እንዲያቀርቡ እድል እና ጊዜ መስጠት በመሆኑ በድንጋጌው የተቀመጠውን የክስ ማሻሻል አላማ የሚያሳካ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም ይግባኝ ሰሚው የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር 1ኛ ተጠሪ ፍቃዳቸውን ያልሰጡበትን ውል መደረጉን ያወቁት መቼ እንደሆነ ገልጸው ክሱን አሻሽለው እንዲያቀርቡ በማድረግ ጉዳዩን እንደገና አጣርቶ እንዲወስን ለስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመመለስ የሰጠው ውሳኔ ከላይ የተመለከቱተን የህግ ድንጋጌዎች እና የሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ሲጠቃለል የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት 1ኛ ተጠሪ ክሳቸውን አሻሽለው እንዲያቀርቡ እና ጉዳዩ እንደገና ተጣርቶ እንዲወሰን ለስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመመለስ የሰጠው ውሳኔ ከላይ በተገለጸው ትንታኔ መሰረት መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ዉሳኔ

1.የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 221271 መጋቢት 20 ቀን 2015 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠዉ ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

2. .የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በግራ ቀኙ ክርክር የሰጠውን ውሳኔ አግባብነት መርምሮ የመሰለውን እንዲወስን በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.341/1/ መሠረት ይመለስለት ብለናል፡፡

3. ግራ ቀኙ የሰበሩ ክርክር ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

4. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ/ጋ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁጥር ....249569

ቀን ጥቅምት 06ቀን 2017ዓ/ም

**ዳኞች፡-** ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ብርሃኑ መንግስቱ

ማርታ ተካ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ሹካሬ በዳዳ -አልቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** 1. መሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን -ጠበቃ አስረስ ረጋሳ -ቀረቡ

2. የሱሉልታ ከተማ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት የቀረበ የለም

3. የሱሉልታ ከተማ አስተዳደር ጉቶ ኖኖ መነ አብቹ ቀበሌ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ይዞታንና ንብረትን የተመለከተ ጉዳይ ሲሆን የተጀመረው በሱሉልታ ወረደ ፍ/ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍ/ቤት አመልካች ከሳሽ ሲሆኑ ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሾች ነበሩ፡፡ የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ የኦሮሚያ ክልል ሸገር ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 45407 ጥቅምት 24 ቀን 2015 ዓ.ም የወረዳዉን ፍ/ቤት ዉሳኔ በመሻር ተሰጥቶ በየደረጃዉ ባሉት

የኦሮሚያ ክልል ፍ/ቤቶች በተሰጡ ዉሳኔዎች የጸናዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በሚል ነዉ፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት፡- አመልካች ከባለቤቴታቸዉ ጋር በነበራቸዉ የንብረት ክፍፍል በመ/ቁጥር 14475 ለፍርድ ቤት ቀርቦ በቀን 24/09/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የክፍፍል ስምምነት ተረጋግጦ የተካፈልኩትን ስፋቱ 1,000 ካሬ ሜትር ላይ ያረፈ ከሳር ክዳን የተሠራ መኖሪያ ቤት እና ይዞታ 1ኛ ተጠሪ ሐምሌ 16 ቀን 2013 ዓ.ም ድንጋይ እና እንጨት በቦታው ላይ በማራገፍ በሕግ አምላክ እየተባለ መሬት አስተዳደር ነው የሰጠኝ በማለት የያዘባቸዉ መሆኑን፤ 2ኛ ተጠሪ ደግሞ ይዞታቸዉ ከእጃቸዉ ሳይወጣ ወይም ካሳና ምትክ ቦታ ሰጥቷቸዉ ሳያስለቅቃቸዉ ያለአግባብ በይዞታቸዉ ላይ ለ1ኛ ተጠሪ ማስረጃ በመስጠቱ እና 3ኛ ተጠሪ ግንቦት 23 ቀን 2013 ዓ.ም ቆሞ ያከፋፈለላቸዉን ንብረት እና

ይዞታ የእኔ ነው በማለት መስጠቱ ሕገ ወጥ ስለሆነ የንብረት ግምት ብር 36,500 ከፍለዋቸዉ ይዞታቸዉን እንዲለቁ እንዲወሰን የሚጠይቅ ነዉ፡፡

1ኛ ተጠሪ ለክሱ የሰጠዉ መልስ ይዘት፡- ክርክር ያስነሳውን ይዞታ ሕጋዊ በሆነ መንገድ የከተማ መሬት ይዞታን ለመስጠት ስልጣን ከተሰጠዉ አካል አግኝተን የባለይዞታ ማስረጃ እና ሊዝ ከመንግስት ጋር የተፈራረምን ስለሆነ እንዲሁም ህጋዊነት ያለው ድርጅት ስለሆነ የቀረበብን ክስ ውድቅ እንዲሆን በማለት ሲጠይቅ፤ 2ኛ ተጠሪ በበኩሉ በሰጠው መልስ ይህንን ይዞታ ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ ከ18 ዓመት በላይ በእጃችን የቆየ ስለሆነ አመልካች ለመክሰስ የሚያስችላቸዉ የባለይዞታነት ማስረጃ ስለሌላቸው የቀረበው ክስ ውድቅ ሊደረግ ይገባል፡፡ በ1996 ዓ.ም ውስጥ ይህንን ይዞታ በልጃቸው በኩል ምትክ የተሰጣቸው ስለሆነ የመንግስት ይዞታ በመሆኑ አመልካች የመክሰስ መብት የላቸውም በማለት ተከራክሯል፡፡ 3ኛ ተጠሪ በሰጠዉ መልስ 1996 ዓ.ም ውስጥ ይህንን ይዞታ በልጃቸዉ በኩል ምትክ ስለተሰጣቸዉ በዚያን ጊዜ አንድም ተቃውሞ አመልካች ሳያነሱ ዛሬ የሚቀርበው የባለይዞታነት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የሱሉልታ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ቤትም በቀረበው መቃወሚያ ላይ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኂላ ውድቅ በማረግ ክርክር ያስነሳው ይዞታ የአመልካች ይዞታ መሆኑንና ካሳ እና ምትክ ሳይከፈል በህገወጥ መንገድ የተያዘባቸው መሆኑ በመረጋገጡ ተጠሪዎች ክርክር ያስነሳው ይዞታ ለአመልካች

በፍ/ሕ/ቁ. 1149/3 እና በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 273 መሠረት ይልቀቁ በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝተዉ ተጠሪዎች ባቀረቡት ይግባኝ መነሻነት ጉዳዩን የተመለከተዉ የፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮና መርምሮ ክርክር የተነሳበት ይዞታ በ1ኛ ተጠሪ ቁጥጥር ሥር የሚገኝ እና ይዞታውን የያዘው በህገወጥ መንገድ መሆኑ ስላልተረጋገጠ 1ኛ ተጠሪ ይዞታዉን ሊለቅ አይገባም፤ ሆኖም ዉሳኔዉ አመልካች ካሳ እና ምትክ ቦታ የመጠየቅ መብት አያግድም በማለት የወረዳ ፍ/ቤት ውሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡ በመቀጠል አመልካች በዉሳኔዉ ቅር ተሰኝተዉ ቅሬታቸዉን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች ቢያቀርቡም ዉሳኔዉን አጽንተዋል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይዘት ባጭሩ፡- 2ኛ ተጠሪ በአመልካች እጅ ባለው እና የአመልካች በሆነው ይዞታ ላይ ለ1ኛ ተጠሪ ካርታ መሥራቱን የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ አረጋግጧል፡፡ ይህ ደግሞ ከሕገ-መንግስቱ፣ ከካሳ አዋጅ እና ከሊዝ አዋጅ

ተቃራኒ መሆኑ እየታወቀ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት የአመልካች ይዞታ በሕጋዊ መንገድ ከእጇ ያልወጣ ቢሆንም 3ኛ ወገን ግን ሕጋዊ በሆነ መንገድ ባለመብት መሆኑን መረዳት ስለሚቻል ይዞታው የ1ኛ ተጠሪ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40(3)፣ በሊዝ አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 26፣ 27 እና ደንብ ቁጥር 182/2008 አንቀጽ 57 መሠረት መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት የተፈጸመበት ነዉ፡፡

የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ በፌዴራሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 40(4) ሆነ በኦሮሚያ ክልል ሕገ መንግሥት መሠረት ባለይዞታ ከመሬት ይዞታዉ ላይ ያለመፈናቀል መብቱ የተከበረ መሆኑ ተደንግጓል፡፡ ነገር ግን ከዚህ የሕገ-መንግሥት ድንጋጌ በተቃራኒ አመልካች ክርክር ባስነሣው ይዞታ ላይ መብት ያላት መሆኗ ተረጋግጦ እያለ በሌላ በኩል ደግሞ 1ኛ ተጠሪ በሕጋዊ መንገድ ይህን ይዞታ ከ2ኛ ተጠሪ ላይ የተሰጠው ስለሆነ አመልካች ምትክ ይዞታ እና ካሳ የመጠየቅ መብት እንዳላት ወስኗል፡፡ ይህ ውሳኔ ከሕገ መንግሥት እና ይህን ሕገ መንግሥት መሠረት አድርገው ከወጡ ሕጐች ጋር ተቃራኒ ነው፡፡ ስለሆነም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በአንድ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

በኩል በአመልካች ይዞታ ላይ የተፈጸመው ድርጊት ከሕገ መንግሥቱ ተቃራኒ መሆኑን እየገለጸ በሌላ በኩል ደግሞ የዚህ ድርጊት ውጤት ሕጋዊ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ ስህተት ነው፡፡

የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በ09/03/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት "ክርክር ያስነሣውን ይዞታ ከአመልካች ላይ 2ኛ ተጠሪ ወስዶ ለ1ኛ ተጠሪ የባለይዞታነት ካርታ የሰጠበት ሁኔታ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ሕግ እና ሕገ መንግሥትን የተከተለ ነው" በማለት የሕግ ጭብጥ ይዟል፡፡ ይሁን እንጂ በሰጠው ውሳኔ ውስጥ ለዚህ ጭብጥ አግባብነት ያለው መልስ ሳይሰጥ አልፎታል፡፡ ፍ/ቤቱ 2ኛ ተጠሪ ለ1ኛ ተጠሪ በራሱ ቁጥጥር ሥር የሚገኘውን ይዞታ/ቦታ/ እንዲተካ ማድረግ ሲገባው የአመልካችን ይዞታ ለ1ኛ ተጠሪ መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ ተሽሮ የሱሉልታ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲጸና የሚጠይቅ ነዉ፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለክርክር መነሻ የሆነው ይዞታ የአመልካች መሆኑንና ምትክ ቦታም ሆነ ካሳ ሳይከፈላቸው በ2ኛ ተጠሪ አማካኝነት ይዞታው ለ1ኛ ተጠሪ መተላለፉ ተረጋግጦ እያለ 1ኛ ተጠሪ ይዞታው በሕጋዊ መንገድ ያገኘው በመሆኑ አመልካች ምትክ ቦታ እና ካሳ ከሚጠይቁ በስቀር 1ኛ ተጠሪ ይዞታውን እንዲለቁ መጠየቅ አይችሉም በሚል መወሰኑ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ-መንግስት አንቀፅ 40(1፣7 እና 8)፤ አዋጅ ቁጥር 1161/2011 እና አዋጁን ለማስፈፀም የወጣው ደንብ ቁጥር 472/2012፤ መንግስት አንድን የግል ንብረት ለህዝብ ጥቅም

በሚወስድበት ጊዜ ሊከተለው ስለሚገባው ሥነ-ሥርዓት በተመለከተ በሰ/መ/ቁ 50810 ከሰጠው አስገዳጅ ትርጉም አንፃር ተገቢነቱን ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ በሰበር ችሎት እንዲታይ የተደረገ ነው፡፡

ተጠሪዎች መልሳቸውን በተናጠል አቅርበዋል፡፡ 1ኛ ተጠሪ የሰጠዉ መልስ ይዘት፡- አመልካች ከመነሻዉ ለክርክር መነሻ የሆነዉ መሬት ከእጇ የወጣበትን ጊዜ እና የወጣበትን አኳኋን በመደበቅ ከባለቤትዋ ጋር በመዝገብ ቁጥር 14475 በሆነ መዝገብ ላይ ተከራክረዉ በቀን 7/9/2013 ዓ.ም በተደረገ ዉል ተከፋፍለዉ ለፍርድ ቤት ቀርቦ በ24/09/2013 ዓ.ም የፀደቀ በማስመሰል ለችሎቱ ያቀረበችዉ ቅሬታ ፈፅሞ ከእዉነት የራቀ ነዉ፡፡ በስር ፍርድ ቤት በማስረጃ ተጣርቶ የተረጋገጠዉ ለክርክር ምክንያት የሆነዉ መሬት በ1983 ዓ.ም ከአመልካች እጅ ወጥቶ እስከ 1996 ዓ.ም ድረስ በአመልካች ልጅ አቶ ታደሰ ለገሰ እጅ የነበረ እና አቶ ታደሰም በዚሁ መዝገብ በስር ፍርድ ቤት

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ ቁጥር 40(2) መሰረት የክርክሩ ተካፋይ የነበረችዉ የአቶ ታደሰ ለገሰ ሚስት ከነበረችዉ ወ/ሮ ሙሉነሽ ኡርጌ ጋር በባልና ሚስትነት ይዘዉት ሲኖሩ በ1996 ዓ.ም የሱሉልታ ከተማ አስተዳደር ጉቶ ኖኖ መነ አቢቹ ቀበሌ አስተዳደር ቦታዉን ለራሱ ለሕዝባዊ ስራ አገልግሎት ስለፈለገዉ ለአመልካቿ ልጅ ለአቶ ታደሰ ለገሰ ሌላ ምትክ ቦታ ከዚሁ ቀበሌ ዉስጥ በመስጠት ቀበሌዉ በባለ ይዞታነት ከ1996 ዓ.ም አንስቶ ይዞት የቆየ ቦታ እንጅ አመልካች በቅሬታዋ ላይ እንደጠቀሰችዉ እስከ 2013 ዓ.ም ድረስ በእጅዋ የነበረ ይዞታ አይደለም፡፡ በሌላ መልኩም ህገ-መንግስትንና አዋጅን እንዲሁም አዋጁን ለማስፈፀም የወጡ ደንቦች በጣሰ መልኩ ለ1ኛ ተጠሪ የተሰጠ የአመልካች የመሬት ይዞታ የለም፡፡ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 40(3) መሰረት ዜጎች መሬት የመጠቀም እንጂ በርስትነት የመያዝ መብት የላቸውም፡፡ በመሆኑም የኢ. ፌ. ድ. ሪ. ሕገ-መንግስት በአንቀፅ 40(1፣ 7 እና 8)፤ አዋጅ ቁጥር 1161/2011 እና አዋጁን ለማስፈፀም የወጣው ደንብ ቁጥር 472/2012 በመጣስ ውሳኔ አለመሰጠቱን ተረድቶ የሰበር አቤቱታው መሰረታዊ የህግ ስህተት አልተፈፀመበትም ተብሎ ውድቅ እንዲደረግ በማለት ተከራክረዋል፡፡

2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችም የ1ኛ ተጠሪ መልስ በይዘቱ የተቀራረበ መልስ በማቅረብ የአመልካች የሰበር አቤቱታቸው ውድቅ እንዲደረግ በመጠየቅ ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም ከተጠሪዎች በቀረበው መልስ ላይ የመልስ መልሳቸውን በማቅረብ የሰበር አቤቱታቸውን በሚያጠናክር መልኩ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን እኛም አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡ የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር መርምረን እንደተረዳነዉ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሻዉ ጭብጥ፡- ለክርክር መነሻ የሆነው ይዞታ የአመልካች መሆኑንና ምትክ ቦታም ሆነ ካሳ ሳይከፈላቸው በ2ኛ ተጠሪ አማካኝነት ይዞታው ለ1ኛ ተጠሪ መተላለፉ ተረጋግጦ እያለ 1ኛ ተጠሪ ይዞታው በሕጋዊ መንገድ ያገኘው በመሆኑ አመልካች ምትክ ቦታ እና ካሳ ከሚጠይቁ በስተቀር 1ኛ ተጠሪ ይዞታውን እንዲለቁ መጠየቅ አይችሉም በሚል መወሰኑ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ-መንግስት አንቀፅ 40(1፣7 እና 8)፤ አዋጅ ቁጥር 1161/2011 እና አዋጁን ለማስፈፀም የወጣው ደንብ ቁጥር

472/2012፣ መንግስት አንድን የግል ንብረት ለህዝብ ጥቅም በሚወስድበት ጊዜ ሊከተለው ስለሚገባው ሥነ-ሥርዓት በተመለከተ በሰ/መ/ቁ 50810 ከሰጠው አስገዳጅ ትርጉም አንፃር ተገቢ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነዉ፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ዳኝነት የጠየቁት ክርክር የያስነሳዉ 1,000 ካ.ሜትር ስፋት ያለዉ ይዞታና ንብረት የአመልካች ሆኖ ሳለ ምንም ዓይነት ካሳና ምትክ ቦታ ሳይሰጣቸዉ ወይም በሕግ አግባብ እንዲለቁ ሳይደረግ 3ኛ ተጠሪ የራሱ ይዞታ እንደሆነ በማረጋገጡ፣ 2ኛ ተጠሪ ለ1ኛ ተጠሪ ይዞታዉን አሳልፎ በመስጠት የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ በመስጠቱ እንዲሁም 1ኛ ተጠሪ ይዞታዉን ያለ አግባብ የያዘዉ በመሆኑ ይዞታቸዉ እንዲለቀቅላቸዉ ነዉ፡፡ ተጠሪዎች በበኩላቸዉ አመልካች በይዞታዉ ላይ የባለይዞታነት መብት የሌላቸዉ መሆኑን፣ በ1996 ዓ.ም አመልካች በልጇ አማካይነት ምትክ ቦታ የተሰጣቸዉ በመሆኑ በሕግ አግባብ ለ1ኛ ተጠሪ ተላልፎ የተሰጠ በመሆኑ ክሱ ዉድቅ እንዲደረግ በመጠየቅ ተከራክረዋል፡፡ የሱሉልታ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮና በማስረጃ አጣርቶ ክርክር ያስነሳዉን ይዞታ አመልካች እስከ 2013 ዓ.ም ድረስ በእጃቸዉ አድርገዉ በእዉነት ያዝዙበት የነበረ መሆኑን፣ ይዞታዉ ለ1ኛ ተጠሪ ሲሰጥ አመልካች በሕግ አግባብ ካሳና ምትክ ቦታ ተሰጥቷቸዉ እንዲለቁ ያልተደረገ ሲሆን ለ1ኛ ተጠሪ በይዞታዉ ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ስልጣን ባለዉ አካል የተሰጠ ቢሆንም አመልካች ይዞታቸዉን ካሳና ምትክ ቦታ ተሰጥቷቸዉ እንዲለቁ ባልተደረገበት ሁኔታ ለ1ኛ ተጠሪ መሰጠቱ ተገቢ አይደለም በሚል ይዞታዉ ለአመልካች እንዲለቀቅ ወስኗል፡፡

በሌላ በኩል የፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የወረዳዉን ፍ/ቤት ዉሳኔ የሻረዉ ክርክር ባስነሳዉ ይዞታ ላይ አመልካች የባለይዞታነት መብት የላቸዉም ወይም

በአመልካች ይዞታ ላይ ተደርቦ ለ1ኛ ተጠሪ ይዞታዉ አልተሰጠዉም በሚል ሳይሆን 1ኛ ተጠሪ ስልጣን ባለዉ አካል ይዞታዉ እና ይዞታዉን የተመለከተ የባለይዞታነት ማረጋገጫ እስከተሰጠዉ ድረስ 1ኛ ተጠሪ ይዞታዉን ሊለቅ አየገባም፡፡ አመልካች የባለይዞታነት መብት አለኝ የሚሉ ከሆነ ምትክ ቦታና ካሳ ሌላ ክስ መስርተዉ ይጠይቁ በሚል ነዉ፡፡ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም በበኩሉ በሰጠዉ ዉሳኔ አመልካች ክርክር ባስነሳዉ ይዞታ ላይ የባለይዞታነት መብት ያላት መሆኑን በማረጋገጥ፣ ሆኖም ይዞታዉ ስልጣን ባለዉ በ2ኛ ተጠሪ አማካይነት ለ1ኛ ተጠሪ

ተላልፎ የተሰጠ በመሆኑ 1ኛ ተጠሪ ይዞታዉን እንዲለቅ ሊደረግ ስለማይገባዉ አመልካች ምትክ ቦታና ካሳ የመጠየቅ መብት ያላቸዉ መሆኑን በማረጋገጥ የከፍተኛዉን ፍ/ቤት ዉሳኔ በዉጤት ደረጃ አጽንቷል፡፡ እዚህ ላይ ምላሽ የሚያሻዉ ነጥብ አመልካች በሕግ አግባብ ይዞታዉን እንዲለቁ ባልተደረገበት ሁኔታ 2ኛ ተጠሪ የአመልካችን ይዞታ 3ኛ ወገን ለሆነዉ ለ1ኛ ተጠሪ አሳልፎ መስጠት ይችላል ወይስ አይችልም? አስተላልፎ ቢገኝስ ይዞታዉ ለአመልካች ተመላሽ ሊደረግ ይገባል ወይስ አመልካች ምትክና ካሳ የመጠየቅ መብት ነዉ ሊጠበቅላቸዉ የሚገባዉ የሚለዉ ነዉ፡፡

በመሠረቱ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 40(8) መንግስት ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘዉ ተመጣጣኝ ካሳ በቅድሚያ በመክፈል የግል ንብረትን የይዞታ መብትን ጨምሮ ለመዉሰድ ይችላል በሚል ተመልክቷል፡፡ ይህ ሕገ-መንግስታዊ ድንጋጌ የግል ባለንብረቶችን ወይም ባለይዞታዎችን ያለአግባብ እንዳይፈናቀሉ ወይም ሌሎች መብታቸዉን ለማስጠበቅ በማሰብ ንብረታቸዉን ወይም ይዞታቸዉን እንዲለቁ ከመደረጉ በፊት አስቀድሞ ካሳ እንዲከፈላቸዉ በጥብቅ ያስቀመጠ ነዉ፡፡ ይህን ድንጋጌ ተግባራዊ ለማድረግ ዝርዝር ድንጋጌዎችን ይዞ የወጣዉ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበት፣ ካሳ የሚከፈልበት እና ተነሺዎች መልሰዉ የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 1161/2011 አንቀጽ 8 ለሕዘብ ጥቅም መሬት የሚለቀቅበትን ሥርዓት በዝርዝር ያስቀመጠ ሲሆን መሬቱ ለተሻለ ሕዝብ ጥቅም እንዲለቀቅ መወሰን፣ ምትክና ካሳ መክፈል ባለይዞታዉን ከማስለቀቅ በፊት የሚወሰኑ ተግባራት መሆናቸዉን ያስቀመጠ ነዉ፡፡ ይህ የሆነዉ ባለይዞታዉ በምትክ በሚሰጠዉ ቦታና የካሳዉ መጠን ላይ አስቀድሞ ክርክር እንዲያቀርብ ብቻ ሳይሆን ለሕዝብ ጥቅም ሲባል እንዲለቅ በተሰጠዉ ዉሳኔ እና በቅድሚያ የማልማት መብቱ በመጠቀም ረገድ አቤቱታዉን ማቅረብ ለማስቻል ጭምር መሆኑን ከአዋጁ አንቀጽ 5/4 እና አንቀጽ 7 ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም አንድ ባለይዞታ ይዞታዉን በሕግ አግባብ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል እንዲለቅ ተወስኖ በቅድሚያ ምትክ ቦታና ካሳ ተከፍሎት ካልሆነ በቀር ይዞታዉን

እንዲለቅ ማድረግ ስለማይቻል እንዲሁም አስቀድሞ በሕግ አግባብ እንዲለቀቅ ባልተደረገ ሁኔታ ይዞታዉን ለሌላ 3ኛ ወገን ወይም አልሚ አሳልፎ መስጠት የይዞታ መደረብን ስለሚያስከትል

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

ይዞታዉ አስቀድሞ ባለይዞታ ለሆነዉ ሰዉ ሊለቀቅለት ይገባል እንጂ ባለይዞታዉ ያለዉ መብት የምትክ ቦታና የካሳ መብት ብቻ እንደሆነ ተቆጥሮ ምትክ ቦታና ካሳ ይጠይቅ ሊባል አይገባም፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ክርክር ያስነሳዉ ይዞታን አመልካች እስከ 2013 ዓ.ም በይዞታቸዉ ስር አድርገዉ በእዉነት ሲያዙበት የነበረ እና በሕግ አግባብ ይዞታዉን እንዲለቁ ዉሳኔ ተሰጥቶበት ምትክ ቦታና ካሳ እንዲያገኙ ያልተደረገ መሆኑን ሁሉም የስር ፍ/ቤቶች የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መዝነዉ በተመሳሳይ አረጋግጠዋል፡፡ አመልካች ይዞታቸዉን ሊያጡ ወይም እንዲለቁ ሊደረግ የሚችለዉ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጸ 40(8) እና በአዋጅ ቁጥር 1161/2011 መሠረት በቅድሚያ በይዞታዉ ላይ የማስለቀቅ ዉሳኔ ተሰጥቶበት፣ ምትክ ቦታና ካሳ ተከፍሎበት መሆን ይገባዋል፡፡ 2ኛ ተጠሪ ይዞታን ለአልሚ ወይም ለሚገባዉ አካል የማስተላለፍና የይዞታ ማረጋገጫ የመስጠት ስልጣን ያለዉ ቢሆንም በሕግ አግባብ እንዲለቀቅ ባለተደረገ የአመልካች ይዞታ ላይ የይዞታ መብት ደርቦ ለሌላ ሰዉ መስጠት ስለማይችል ለ1ኛ ተጠሪ የተሰጠዉ የይዞታ ማረጋገጫ የአመልካችን የባለይዞታነት መብት የሚያሳጣ አይሆንም፡፡ ስለሆነም አመልካች ይዞታቸዉን ከሕግ አግባብ ዉጪ ተወስዶባቸዉ ባለበት ሁኔታ ይዞታዉ እንዲለቀቅላቸዉ ሊወስን እየተገባ የስር ፍ/ቤቶች ምትክ ቦታና ካሳ ይጠይቁ መባሉ ተገቢ አይደለም፡፡ ይልቁንም ተገቢ የሚሆነዉ የአመልካች ይዞታ እንዲመለስላቸዉ ሲወሰን ስልጣን ያለዉ አካል ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትን የሕግ ሥርዓት ተከትሎ ይዞታዉን የማስለቀቅ ስልጣኑ በዉሳኔዉ የማይነካ መሆኑን ማመላከቱ ነዉ፡፡

ሲጠቃለል ክርክር ያስነሳዉ ይዞታ የአመልካች ሆኖ በሕግ አግባብ እንዲለቁ ያልተደረገ መሆኑ በሁሉም የስር ፍ/ቤቶች በተረጋገጠበት ሁኔታ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ችሎቶች 1ኛ ተጠሪ በይዞታዉ ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ስልጣን ባለዉ አካል የተሰጠዉ መሆኑን ብቻ በመመልከት አመልካች ክስ አቅርበዉ ምትክ ቦታና ካሳ የመጠየቅ መብታቸዉን በመጠበቅ 1ኛ ተጠሪ ይዞታዉን ሊለቅ አይገባም በማለት የወረዳዉን ፍ/ቤት ዉሳኔ በመሻር የሰጡት ዉሳኔ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 40(8) እና የአዋጅ ቁጥር 1161/2011 ድንጋጌዎች የተቀመጠዉን ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትን ሥርዓት ያላገናዘበ እና በፌዴራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሀ) እና 10(1/ሐ) መሠረት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. በኦሮሚያ ክልል በሸገር ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 45407 ጥቅምት 24 ቀን 2015 ዓ.ም ተሰጥቶ፤ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 411263 የካቲት 14 ቀን 2015 ዓ.ም በተሰጠ ዉሳኔ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎ በመ/ቁ 422131 መጋቢት 21 ቀን 2015 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ የጸናዉ ዉሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1/ለ) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የሱሉልታ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 15213 ግንቦት 15 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ ጸንቷል፡፡
3. ከዚህ በኃላ ስልጣን ያለዉ አካል ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትን የሕግ ሥርዓት ተከትሎ ለአመልካች ምትክ ቦታና ካሳ በመክፈል ይዞታዉን ከማስለቀቅ ይህ ዉሳኔ አያግድም ተብሏል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

የሰ/መ/ቁጥር---249641
ቀን- ጥቅምት 05 ቀን 2017 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ብርሃኑ መንግስቱ

ማርታ ተካ

**አመልካች**: - የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ዐ/ሕግ - ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- ኮ/ል እናዉ መገርሳ ማሞ - አልቀረበም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ጉዳዩ ወንጀል ሲሆን የተጀመረዉ አመልካች በኦሮሚያ ክልል ቡኖ በደሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ በመሠረተዉ ክስ መነሻነት ነዉ፡፡ የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 422074 ሚያዚያ 03 ቀን 2015 ዓ.ም የስር ፍ/ቤቶችን ዉሳኔ በማሻሻል የሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በሚል ነዉ፡፡

የክሱ ይዘት፡- ተጠሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 671(1/ለ) ስር የተመለከተዉን በመተላለፍ በቡኖ በደሌ ዞን መኮ ወረዳ መኮ ከተማ ቀበሌ 01 ልዩ ስሙ ዋቲ በሚባል ስፍራ ደሱ ተስፋዬ የተባለ የግል ተበዳይን ከጓደኞቹ ጋር ፑል በመጫወት ላይ እያለ ወደ እሱ ሄዶ ትፈለጋለህ ብሎ ወደ ውጪ ካስወጣው በኋላ ይዞት ባለው

የጦር መሳሪያ በሰደፍ ሰውነቱ ላይ ከመታው በኋላ ቆሻሻ የሚጣልበት ቦታ በመውሰድ ይዞት የነበረውን ክላሽ አቀባብሎ ገድዬህ ደምህን እጠጣለሁ፤ ዛሬውኑ ያበቃልሀል ተሰናበት፤ ቆለጥህ ላይ መትቼህ ያለልጅ አስቀርሃለሁ ብሎ ተጠሪ ጥይቱን በማውጣት አፉ ውስጥ በማስገባት አስፈራርቶት የጭንቅላቱን ፀጉር እና ፂምን ነጭቶ ቁጭ ብድግ በል ብሎት ከፍተኛ ፍርሀት ካደረሰበት በኋላ ራሱን እንዳይከላከል አድርጎ ብር 5,000 (አምስት ሺ ብር) የወሰደበት በመሆኑ በፈጸመዉ በከባድ የውንብድና ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

በቡኖ በደሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ የእምነት ክህደት ቃሉን እንዲሰጥ ተጠይቆ በሰጠው ቃል ተበዳዩ ከዚህ በፊት ታጥቆ ጫካ ካለው አካል ጋር ትስስር አለው ተብሎ ታስሮ በመውጣቱ አሁንም ወደ ሳቺ አካባቢ የጠላት እንቅስቃሴ አለ የሚባል መረጃ ስላለ እሱን ለማጣራት ተበዳይን ከመጠየቅ ውጪ የተከሰስኩበትን የወንጀል ድርጊት አልፈፀምኩም በማለት ክዶ በመከራከሩ ፍ/ቤቱ የዐ/ህግ ምስክር ሰምቶ እንዲከላከል ብይን የሰጠ ቢሆንም ተጠሪ የመከላከያ ማስረጃ ማቅረብ ስላልቻለ የተከሰሰበት ድርጊት መፈፀሙ በማረጋገጥና ክስ በቀረበበት የወ/ሕግ አንቀጽ 671(1/ለ) ድንጋጌ የተመለከተዉን በመተላለፍ ጥፋተኛ በማድረግ በ7 ዓመት ከ8 ወር ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝቶ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ በመቀጠል ተጠሪ የሰበር አቤቱታ ያቀረበለት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙን አከራክሮና መርምሮ ተጠሪ ጥፋተኛ የተባለበትን የሕግ ድንጋጌ ወደ ወንጀል ሕግ አንቀጽ 590(1/ሐ) በመለወጥና ቅጣቱንም በ2 ዓመት ከ6 ወር ቀላል እስራት እንዲቀጣ በማድረግ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡትን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ አሻሽሎ ውስኗል፡፡ አቤቱታ የቀረበውም ይህንን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ በመቃወም ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካች ያቀረበዉ የሰበር አቤቱታ ይዘት በአጭሩ፡- የዐ/ሕግ ምስክሮች በአንድ ቃል ተጠሪ የጸረ አማጺ ፖሊስ አባል ሆኖ የግል ተበዳይ እየተጫወተ በሚገኝበት ቦታ ይዞት በነበረዉ የጦር መሳሪያ ክላሽ በሰደፉ ደረቱ ላይ መትቶት ቆሻሻ በሚደፋበት ጉድጓድ አፋፍ ላይ በመውሰድ ገድዬህ ደምህን እጠጣለሁ፤ ቆለጥህን መትቼ ያለልጅ አስቀርሃለሁ በማለት ሲዝትበት ከቆየ በኋላ የክላሽ ጥይቱን አውጥቶ አፉ ውስጥ በማድረግ የጭንቅላቱን እና የጺሙን ጸጉር በመንጨት ስቃይ ካደረሰበት በኋላ ብር 5,000 (አምስት ሺህ ብር) ከኪሱ ቦርሳ ውስጥ ዘርፎት መሄዱን ከበቂ በላይ በሆነ ሁኔታ ተረጋግጧል፡፡ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 671(1)(ለ) ከሚያቋቁመው ፍሬ ነገሮች ዉስጥ ተበዳዩን አደገኛ በሆነ ሌላ ዓይነት መሣሪያ በማስፈራራት ወይም ስቃይ በሚያደርስ ሁኔታ በማንገላታት ወይም ከባድ የአካል ጉዳት ማድረሱን የቡኖ በደሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪን ጥፋተኛ መሆኑን በማረጋገጥ ያስተላለፈው የጥፋተኝነት ውሳኔ እና በ7 ዓመት ከ8 ወር በጽኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ ይህ ውሳኔ የሚነቀፍበት ምክንያት የለም፡፡ ሆኖም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤቶቹን ውሳኔ በማሻሻል ተጠሪ ጥፋተኛ ሊባል የሚገባው በወንጀል ሕግ አንቀፅ 671/1/ለ ሳይሆን በወንጀል ህግ አንቀፅ 590(1)(ሐ) እና (2ሀ) ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ መባል

ይኖርበታል በማለት" በመለወጥ ጥፋተኛ አድርጎ ቅጣቱን ወደ 2 ዓመት ከ 6 ወር ቀላል እስራት መቀየሩ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተሽሮ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንዲፀና የሚጠይቅ ነዉ።

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ በስር ፍርድ ቤቶች ስለመፈፀማቸው ከተረጋገጠው የወንጀል ድርጊት አንፃር የተጠሪ የወንጀል ተግባር የሚያቋቁመው የመንጀል ሕግ አንቀፅ 671(1/ለ)ን ነው? ወይስ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 590(1/(ሐ) እና 2/ሀ)ን? የሚለውን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ነዉ።

ተጠሪ ጥር 14 ቀን 2016 ዓ.ም የተዘጋጀ 3 ገጽ መልስ ያቀረበ ሲሆን ይዘቱም፡- በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10/1/ሐ፣መ/ ስር የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የክልል ጉዳዮችን በሰበር የሚያየዉ ቅሬታ የቀረበበት ዉሳኔ ህገ መንግስቱን የሚቃረን ከሆነ ወይም አስገዳጅ የህግ ትርጉምን የሚቃረን ከሆነ ወይም ሀገራዊ ጥቅም ባላቸዉ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ሕግን አለግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የላሌውን ሕግ የሚጠቅስ ከሆነ ነዉ። የትኛው መሰረታዊ የህግ ስህተት እንደተፈፀመ በአቤቱታው አልተገለፀም። የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ 422074 ላይ የሰጠ ዉሳኔ ከህገ መንግስቱ ጋር የሚቃረን አይደለም፤ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አስገዳጅ ዉሳኔ ጋርም የሚጣረስ አይደለም። እንዲሁም ጉዳዩ ሀገራዊ ጥቅም ያለዉ አይደለም። ስለዚህ ሰበር ችሎቱ ይህንን ጉዳይ በሰበር-ሰበር ለማየት ስልጣን ስለሌለዉ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል መሰረታዊ የህግ ስህተት የለዉም ተብሎ ዉድቅ ሊደረግ ይገባል።

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በመዝገብ ቁጥር 37256 ላይ የወንጀል ክስ የማስረጃ ምዘና መርህ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ የፀዳ/Beyond reasonable doubt/ መሆን እንዳለበት አስገዳጅ ትርጓሜ ሰጥቷል። የዐቃቤ ህግ ምስክሮች ተጠሪ ከግል ተበዳይ ብር መዉሰዱን ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በፀዳ መልክ አላረጋገጡም። ተጠሪ ገንዘብ መዉሰዱ በምስክር ሳይረጋገጥበት ደግሞ የዉንብድና ወንጀል መፈጸሙ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ ተብሎ በሰበር ሰሚ ችሎቱ የተያዘዉ ጭብጥ ላይ መገለጹ ስህተት ስለሆነ የአመልካች አቤቱታ ዉድቅ እንድደረግልኝ። ቡኖ በደሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምዕራብ ምድብ ቋሚ ችሎት ተጠሪን በዓቃቤ ህግ ምስክር ሳያረጋግጥበት በከባድ የዉንብድና ወንጀል መቅጣታቸዉ ዉጤቱ ሲታይ ያለግባብ ፍትህን ያዛባ ዉሳኔ መሆኑን ተረድቶ ያስተካከለ ስለሆነ በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ትርጓሜ አዋጅ ቁጥር 216/2011 መሰረት ያደረገ ከሚበል በስተቀር ስህተት የሌለው የለዉም። የዐቃቤ ህግ ምስክሮች ተጠሪ አስገድዶ ገንዘብ መቀበሉ ጋር ተያይዞ እርስ በርስ የሚጣረስ ምስክሪነት ሰጥቶ እያለ የስር ፍርድ ቤቶች የዐቃቤ ህግ ምስክር በሙሉ አለመመዘናቸዉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ይህንን ማስተካከሉ ተገቢ ነዉ። የወንጀል ህግ አንቀጽ 671 ስር የሚያስቀጣ በጉልበት የተፈጸመዉ ድርጊት የተበዳይ ንብረት ከመዉሰድ ጋር የሚያያዝ ከሆነ ነዉ። በዚህ ጉዳይ ዉስጥ ተጠሪ ብር ወስዷል ተብሎ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በክስ ላይ ከመገለጽ ዉጭ ገንዘቡን መዉሰዱ አልተረጋገጠም፡፡ ስለዚህ ተጠሪ ከስራዉ ሁኔታ ጋር በተያያዘ ከባድ ማስፈራርያ በግል ተበዳይ ላይ በማድረሱ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በ1996 ዓ.ም የወጣዉ የኢ.ፌ.ደ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 590/1/ሐ/ እና 2/ሀ/ ስር የተሰጠ የጥፋተኝነት ዉሳኔ ትክክል ነዉ ተብሎ እንዲፀና እና የቀረበ አቤቱታ ዉድቅ እንዲደረግለት በመጠየቅ ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን የአመልካችን አቤቱታ ከስር ፍ/ቤቶች ብይን እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ አቤቱታዉ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሻዉ ጭብጥ፡- በስር ፍርድ ቤቶች በተጠሪ ስለመፈፀማቸው ከተረጋገጡ የወንጀል ድርጊት ፍሬ ነገሮች አንፃር የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪ ገንዘብ መወሰዱን 2 የዐ/ሕግ ምስክሮች ቢመሠክሩም ሌሎች 2 ምስክሮች ገንዘብ መወሰዱን አለማየታቸዉን ከመመስከራቸዉ አንጻር የተጠሪ የወንጀል ተግባር የሚሸፈነዉ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 671(1/ለ) ሳይሆን በወንጀል ሕግ አንቀፅ 590(1/(ሐ) እና 2/ሀ) ነዉ በማለት የጥፋተኝነትና የቅጣት ዉሳኔዉን አሻሽሎ መወሰኑ ተገቢ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነዉ፡፡

ማስረጃን መዝኖ ፍሬ ነገርን ለማረጋገጥ ስልጣን የተሰጠዉ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ዐ/ሕግ ክሱን ለማስረዳት ያቀረባቸዉን የአራት ምስክሮች ቃል ሰምቶና መዝኖ ተጠሪ የግል ተበዳይ ከጓደኞቹ ጋር ፑል ይጫወትበት ከነበረበተ ቦታ በመሄድ ታጥቆ ጫካ ያለዉን አካል ትደግፋለህ ብሎት የግል ተበዳይንና 2ኛ የዐ/ሕግ ምስክርን ከፑል ቤቱ አስወጥቷቸዉ እና የጦር መሳሪያ ደግኖባቸዉ በአካባቢዉ ወዳለዉ የቆሻሻ ጉድጓድ ወስዷቸዉ ቁጭ ብድግ ካስደረጋቸዉ በኃላ የግል ተበዳይን የጺም ፀጉር በመንጨትና ያለልጅ አስቀረሃለዉ በሚል ዝቶበት በሰደፍ ደረቱን በመምታትና በጥፊም በመምታት አስፈራርቶት ከኪሱ ብር 5,000 በመዉሰድ የግል ተበዳይን የተወሰነ ጊዜ አቆይቶት የመለሰዉ መሆኑን 1ኛ እና 3ኛ የዐ/ሕግ ምስክሮች ማረጋገጣቸዉን፤ 2ኛ የዐ/ሕግ ተንበርክኮ ከግል ተበዳይ በተቃራኒ ዞሮ ስለነበረ ተጠሪ በቀጥታ ከግል ተበዳይ ገንዘብ መዉሰዱን አለማየቱ ከ3ኛ ምስክር አመሰካከር ጋር የሚጣጣም መሆኑን በመግለጽ ተጠሪ በግል ተበዳይ ላይ የኃይል ተግባር እና በመሳሪያ በማስፈራራት ብር 5,000 የወሰደበት መሆኑን በማረጋገጥ የወ/ሕ/አንቀጽ 671(1/ለ) የተመለከተዉን በመተላለፍ የከባድ ዉንብድና ወንጀል በመፈጸሙ ጥፋተኛ ብሎታል፡፡ ማስረጃ በመመዘንና ፍሬ ነገርን በማረጋገጥ ረገድ የመጨረሻ ዉሳኔ የመስጠት ስልጣን ያለዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ይህንኑ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ድምዳሜና የጥፋተኝነት ዉሳኔ ተቀብሎታል፡፡

በሌላ በኩል የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ተጠሪ ጥፋተኛ የተባለበትን የወ/ሕግ አንቀጽ 671(1/ለ) የተመለከተዉን ወደ የወ/ሕግ አንቀጽ 590(1/ሐ) እና 2/ሀ) በመለወጥ የጥፋተኝነት ዉሳኔዉን ሲያሻሽል የሰጠዉ ምክንያት ተጠሪ በግል ተበዳይ ከባድ የማንገላታት እና የኃይል ድርጊት ቢፈጽምም ብር 5,000

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ከግል ተበዳይ መዉሰዱ አልተረጋገጠም፡፡ ምክንያቱም ገንዘቡን ተጠሪ መዉሰዱን የግል ተበዳይ የሆነዉ 1ኛ ምስክርና 3ኛ ምስክር ቢመሰክሩም 2ኛ እና 4ኛ የዐ/ሕግ ምስክሮች ተጠሪ ገንዘብ ሲወስድ አለማየታቸዉን የመሠከሩ በመሆናቸዉ ገንዘብ ወስዷል የሚለዉ ምስክርነት እምነት የሚጣልበት አይደለም፡፡ ይህም በክልሉ አዋጅ ቁጥር 216/2011 አንቀጽ 26(2/ሐ) መሰረት ፍትህን ያዛባ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለዉ በሚል ነዉ፡፡

በመሠረቱ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 80(3/ለ) ለክልል ሰበር ችሎቶች የተሰጠዉ ስልጣን በክልል ጉዳዮች በተሰጠ የመጨረሻ ዉሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ማረም ነዉ፡፡ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ፍ/ቤቶች አደረጃጀት፣ ስልጣን እና ተግባር እንደገና ለመወሰን የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 216/2011 አንቀጽ 25(2/ረ) መሰረት የክልሉ ሰበር ችሎት አንድን የክልል ጉዳይ ተመልክቶ ማረም የሚችለዉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበት ሲገኝ ሲሆን የአዋጁ አንቀጽ 26(2) ደግሞ አንድ የመጨረሻ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለዉ የሚባለዉ የሕግ ትርጉም ወይም መሠረታዊ የሕግ መርሆ ስህተት ካለበት ወይም ግልጽ የሆነ የሕግ ድንጋጌ ጥሰት ካለበት እና በሰዎች መብት ላይ ወይም በፍትህ ስርዓቱ ላይ አላስፈላጊ ተጽዕኖ አስከትሎ ከሆነ፤ ወይም መሠረታዊ የሰብዓዊ መብት እና ነጻነት ያለአግባብ ያሳጣ ወይም ያጣበበ እንደሆነ፤ ወይም ያለአግባብ ፍትህን ያዛባ ወይም የጣሰ ከሆነ እንደሆነ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለዉ በአዋጁ አንቀጽ 26(2) የተደነገጉትን መሠረታዊ የሕግ ስህተት መስፈርት ያላሟላ ስህተት ቢኖር እንኳ በክልሉ ሰበር ችሎት ለመታየት ብቁ የማያደረገዉ መሆኑን ሲሆን በተለይ ማስረጃ ምዘናና ፍሬ ነገርን በማረጋገጥ ረገድ የክልሉ ሰበር ችሎት ስልጣን ያልተሰጠዉ መሆኑን ነዉ፡፡ ስለሆነም የክልሉ ሰበር ችሎት የማስረጃ አቀራረብን፣ አግባብነትና ተቀባይነት፣ የማስረዳት ሸክምና የማስረጃ ምዘናን የሚመለከቱ መሠረታዊ መርሆች ጥሰትን ከማረም በስተቀር ማስረጃ ለመመዘንና ፍሬ ነገርን በማረጋገጥ የመጨረሻ ዉሳኔ ለመስጠት ጭምር ስልጣን በተሰጣቸዉ የስር ፍ/ቤቶች ማስረጃ ሰምተዉና መዝነዉ የደረሱበትን የፍሬ ነገር ድምዳሜ ወደ ጎን በመተዉ ማስረጃዉን በድጋሚ የመመዘን ተግባር የሚፈጽምበት አግባብ የለም፡፡ ይህን በሚያጠናክር መልኩ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 187484 እና በሌሎች መዛግብት አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

ማስረጃ ለመመዘንና ፍሬ ነገርን ለማረጋገጥ ስልጣን የተሰጣቸዉ የስር ፍ/ቤቶች ማስረጃ ሰምተዉና መዝነዉ ተጠሪ በግል ተበዳይ ከባድ እንግልትና ማስፈራራት ተግባር ከመፈጸሙም በላይ ከግል ተበዳይ ኪስ ብር 5,000 በመዉሰድ የመለሰዉ መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት 1ኛ እና 3ኛ የዐ/ሕግ ምስክሮች ብር 5,000 ተጠሪ ወስዷል ሲሉ የመሠከሩትን እንዴት 2ኛ እና 4ኛ ምስክሮች ገንዘብ ሲወሰድ ሳያዩ ቻሉ በሚል በቀጥታ ማስረጃዉን በመመዘን ብር 5,000 ተጠሪ ወስዷል የሚለዉ ምስክርነት እምነት የሚጣልበት አይደለም የሚል ምክንያት በመስጠት ተጠሪ በግል ተበዳይ ላይ የከባድ እንግልትና የኃይል ተግባር ፈጽመ እንጂ ገንዘቡን አልወሰደም የሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ ጥፋተኛ የተባለበትን የሕግ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አንቀጽና ቅጣት በማሻሻል ወስኗል፡፡ ይህ የክልሉ ሰበር ችሎት ዉሳኔ የማስረጃ ምዘናና ፍሬ ነገርን የማረጋገጥ ጉዳይ በመሆኑ ከተሰጠዉ ስልጣን ዉጭ በመዉጣት እንደገና ማስረጃ የመዘነ ከመሆኑም ባሻገር ማስረጃ ምዘናዉም ቢሆን 2ኛ እና 4ኛ የዐ/ሕግ ምስክሮች ተጠሪ ገንዘብ ሲወስድ አለማየታቸዉን እንጂ ገንዘቡን አልወሰደም በማለት ያላረጋገጡ በመሆናቸዉ እንዲሁም ተጠሪ ገንዘቡን ከተበዳይ ኪስ ወስዷል በተባለበት ቅጽበት 2ኛ የዐ/ሕግ ምስክሩ ተጠሪ አስበርክኮት እይታዉ ከግል ተበዳይ በተቃራኒዉ ስለነበረ አለማየቱ ከሌሎች ምስክሮች ምስክርነት ጋር እንደማይጋጭ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠዉን ምክንያት ግምት ዉስጥ ያላስገባ ነዉ፡፡ ስለሆነም የክልሉ ሰበር ሰሚ የምስክሮችን ቃል እንደገና በመመዘን የስር ፍ/ቤቶችን ዉሳኔ መሻሩ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 80(3/ለ) የተሰጠዉን መሠረታዊ የሕግ ስህተት የማረም ስልጣንና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 187484 እና በሌሎች መዛግብት የሰጠዉን ገዥ ትርጉም ያላገናዘበ ነዉ፡፡

ከላይ ከተገለጸዉ በተጨማሪ ተጠሪ በግል ተበዳይ ላይ የኃይል ተግባር በመፈጸም ብር 5,000 መዉሰዱ በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጦ ባለበት ሁኔታ የዐ/ሕግ ምስክሮች ቃል እምነት የሚጣልበት አይደለም በሚል ተጠሪ ገንዘብ አልወሰደም የሚል የተሳሳተ ድምዳሜ ላይ ከደረሰ በኃላ የተሳሳተዉን ድምዳሜ መሠረት በማድረግ የስር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ ያለአግባብ ፍትህ ተዛብቷል፤ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ የክልሉን አዋጅ ቁጥር 216/2011 አንቀጽ 25(2/ረ) እና 26(2/ሐ) ድንጋጌዎችን ያላገናዘበ ነዉ፡፡

ሲጠቃለል የኦሮሚያ ክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ማስረጃ ለመመዘንና ፍሬ ነገርን ለማረጋገጥ ስልጣን የተሰጣቸዉ የስር ፍ/ቤቶች ያረጋገጡትን ፍሬ ነገር ወደ ጎን በመተዉ እንደገና የማስረጃ ምዘና በማድረግ ተጠሪ የከባድ እንግልትና የኃይል ተግባር መፈጸሙ እንጂ ብር 5,000 ከግል ተበዳይ መዉሰዱ አልተረጋገጠም በሚል ተጠሪ ጥፋተኛ የተባለበትን የወ/ሕግ አንቀጽ 671(1/ለ)ድንጋጌ ወደ የወ/ሕግ አንቀጽ 590(1/ሐ እና 2/ሀ) በመለወጥ በስር ፍ/ቤት የተሰጠዉን የጥፋተኝነትና የቅጣት ዉሳኔ በማሻሻል የሰጠዉ ዉሳኔ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 80(3/ለ)፤ የክልሉን አዋጅ ቁጥር 216/2011 አንቀጽ 25(2/ረ) እና 26(2) ድንጋጌዎችን እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 187484 እና በሌሎች መዛግብት የሰበር ችሎት ስልጣንን አስመልክቶ የሰጠዉን ገዥ ትርጉም ያላገናዘበ እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሀ እና ሸ) እና አንቀጽ 10(1) መሠረት መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የኦሮሚያ ክልል ሰበር ችሎት በመ/ቁ 422074 ሚያዚያ 03 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት በተሰጠ ዉሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1/ለ) መሠረት ተሽሯል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

2. በቡኖ በደሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 05025 ጥር 15 ቀን 2015 ዓ.ም ተሰጥቶ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 425089 የካቲት 07 ቀን 2015 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ የጸናዉ የጥፋተኝነትና የቅጣት ዉሳኔ ጸንቷል፡፡

3. የቡነ በደሌ ዞን ማረሚያ ቤት አስተዳደር የክልሉ ሰበር ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ ተሽሮ የቡናኖ በደሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠዉ የጥፋተኝነትና የቅጣት ዉሳኔ መጽናቱን አዉቆ በዚሁ አግባብ ቀሪዉን የጽኑ እስራት ቅጣት እንዲያስፈጽም ታዟል፡፡ ይጻፍ፡፡

4. መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሠ/መ/ቁጥር 249962

ጥቅምት 25 ቀን 2017ዓ/ም

ዳኞች ፡- ብርሀኑ አመነው

በዕዉቀት በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ብርሃኑ መንግሥቱ

ማርታ ተካ

አመልካቾች፡- 1. አቶ ጀማል ጉለድ

2. አቶ አብድየሬ ቡራሌ አልቀረቡም

3. አቶ ሽኔ ቡራሌ

ተጠሪዎች ፡- 1. አቶ መሀመድ አህመድ

2. አቶ አብዱ አህመድ

3. ወ/ሮ ኢፍራህ አህመድ ጠበቃ አጥሉ ሀብታሙ ቀረቡ

4. አቶ ሀሰን አህመድ

5. አቶ አሊ አህመድ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በመሬት ይዞታ ላይ ተፈጠረ የተባለዉን የሁከት ተግባር ለማስወገድ የቀረበ ክስ ተከትሎ የተሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል የቀረበ የሰበር አቤቱታ የሚመለከት ነዉ፡፡ክርክሩ የተጀመረው በሶማሌ ክልል መንግስት የፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪዎች በአመልካቾች ላይ በመሠረቱት ክስ - በጅግጅጋ ከተማ ቀበሌ 04 ዉስጥ የሚገኘዉንና አዋሳኞቹ የተጠቀሰዉን 187.5 ካሬ ሜትር ቦታ አመልካቾች ሁከት ፈጥረዉ ስለያዙ ሁከት እንዲወገድ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካቾች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማስቀደም በሰጡት መልስ በእኛ ይዞታ ላይ ሁከት የፈጠሩብን ተጠሪዎች ናቸዉ እንጂ እኛ በተጠሪዎች ይዞታ ላይ የፈጠርነዉ የሁከት ተግባር ስለሌለ ክሱ ዉድቅ ይደረግልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ በመ/ቁጥር 052-328-214 ላይ በቀን 13/03/2015ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ አመልካቾች በክሱ ላይ በተጠቀሰዉ የመሬት ይዞታ ላይ የሁከት ተግባር መፈጸማቸዉን ማረጋገጡን በመግለጽ ሁከት እንዲወገድ ወስኗል፡፡ተጠሪዎች በዉሳኔዉ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለሱማሌ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዉ ችሎቱ በመ/ቁጥር 05-1-119/15 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 29/05/2015 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ጉድለት የለበትም በማለት አጽንቷል፡፡በመቀጠል አመልካቾች የሰበር አቤቱታቸዉን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ቢሆንም ችሎቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ በመ/ቁጥር 05-1-242/15 በቀን 02/09/2015ዓ/ም በአብላጫ ድምጽ በሰጠዉ ዉሳኔ በየደረጃዉ ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠዉ ዉሳኔ ጉድለት የለበትም በማለት አጽንቷል፡፡

አመልካቾች ሰኔ 28 ቀን 2015 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታቸዉ አጭር ይዘት፡- የሥር ፍርድ ቤት የአመልካቾችን ማስረጃ ሳይሠማ ክርክራችንን ውድቅ ማድረጉ የተከራካሪ ወገኖችን የመሰማት፣የመከላከል መብት ብሎም በእኩልነት መርህ የመዳኘት መብት የሚጥሥ በመሆኑ በሰ/መ/ቁጥር 52546 ላይ የተሰጠዉን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሚጥስ ነዉ፡፡የስር ፍርድ ቤት ለዉሳኔዉ መሠረት ያደረገዉ ማስረጃ በግራ ቀኝ ተከራካሪዎች ከተዘረዘሩ ምስክሮች ውጪ በግልጽ ችሎት ሳይቀርቡ፣መኃላ ሳይፈጽሙ እና በግራ-ቀኛችን መስቀለኛ ጥያቄ ሳይጠየቁ ፍርድ ቤቱ አከራካሪ ይዞታውን ለማየት በሄደበት ጊዜ ያገኛቸውን ጎረቤቶች ሰምቶ ውሳኔ መስጠቱ አግባብ አይደለም፡፡በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1149/1 ድንጋጌ ላይ በተመለከተዉ መሰረት አመልካቾች ይዞታ ስር የሚገኘዉን ይዞታ ተጠሪዎ ሁከት ፈጥረን የያዝንባቸዉ ስለመሆኑ በማስረጃ ባላረጋገጡበት እና ተገቢዉ ጭብጥ ሳይያዝ የተሰጠው ውሳኔ በሰ/መ/ቁጥር 80241 እና 37391 ላይ የተሰጠዉን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሚቃረን ነዉ፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ችሎቱ የሰበር አቤቱታዉንና በክልሉ በየደረጃዉ ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠ ዉሳኔ በመመርመር የሥር ፍርድ ቤቶች የግራ ቀኙን ማስረጃ በአግባቡ ሳይሰሙ እና የይዞታዉን ጎረቤቶች ሰምቻለው በሚል ተከራካሪ ወገኖች ምስሮችን ለመጠየቅና ለመፈተን እድል ሳይሰጣቸው አመልካቾች የፈጠሩት ሁከት ይወገድ በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ ይህ ሰበር ችሎት ከፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1149 አተገባበር አኳያ፣ እንዲሁም ከመሰረታዊ የክርክር አመራር እና የማስረጃ ምዘና መርህ አተገባበር አንፃር በሰ/መ/ቁጥር 43081 እና 52545 ላይ የሰጣቸውን ገዥ ትርጉሞች የተከተለ መሆን አለመሆኑ እንዲመረመር ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ አዝዟል።

ተጠሪዎች በቀን 15/09/2016 ዓ.ም በተጻፈ መልስ ሰበር ችሎት ማስረጃን መመርመር እና የመመዘን ሥልጣን ስለሌለዉ የተያዘዉ ጭብጥ አግባብነት የለዉም።ያልተሰሙ ምስክሮች በሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች የተቆጠሩት በመሆናቸው በአመልካቾች ላይ የተፈፀመ መድሎ የለም። አመልካቾች ሳይታይላቸው የቀረው ማስረጃ ምን እንደሚያስረዳ ያላስረዱ በመሆኑ ከዚህ አኳያ የቀረበው የአመልካቾች ቅሬታ ተቀባይነት የለውም። ከጭብጥ አመሠራረት አኳያ የተፈጸመ ስህተት የለም። ፍርድ ቤቶች የቀረበላቸውን ጉዳይ አይተው ለመወሰን ስልጣን የሌላቸው እንደሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 9(1 እና 2) መሰረት በተከራካሪ ወገኖች ጥያቄ ባይቀርብላቸውም በራሳቸው አነሳሽነት ጉዳዩን አንስተው ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት መምራት እንደሚጠበቅባቸዉ በሰ/መ/ቁጥር 102543 ላይ አስገዳጅ ትርጉም ተሰጥቶ እያለ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባልተሰጠው ስልጣን የሁከት ይወገድልኝ ክስ ሰምቶ የሰጠዉ ውሳኔ መሆኑን በመገንዘብ ተጠሪዎች ከፈለጉ ለወረዳው ፍርድ ቤት ክስ የማቅረብ መብታቸው ተጠብቆ ውሳኔ እንዲሰጥልን ካልሆነም በውጤት ደረጃ የሚነቀፉ ውሳኔዎች ባለመሆናቸው እንዲፀናልን በማለት ተከራክረዋል። አመልካቾችም የመልስ መልሳቸውን በማቅረብ ተከራክረዋል።

ከላይ በአጭሩ የተመለከተዉ የግራ ቀኙን ክርክርና በየደረጃዉ በክልሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠ ዉሳኔ ይዘት የሚመለከት ሲሆን እኛም አስቀድሞ ተይዞ የነበረዉን ጭብጥ በመለወጥ የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክሱን ሰምቶ ለመወሰን የሚያስችል የሥረ-ነገር ዳኝነት ሥልጣን አለው ወይስ የለውም? የሚለውን በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን እንደሚከተለው መርምረናል።

እንደመረመርነዉም የፍትሐ ብሔር ክርክር የፌዴራል ወይም የክልል ጉዳይ መሆኑን ታሳቢ ባደረገ አኳኋን በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት፣ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ፣ጉዳዩ ከሚመለከተዉ ክልል ሕገ መንግሥት፣ ጉዳዩ ከሚመለከተዉ ክልል ፍርድ ቤቶች አዋጅ እና ሥነ ሥርዓታዊ ባህርይ ያላቸዉን ልዩ ልዩ ድንጋጌዎችን በያዙ በሌሎች ልዩ ሕግጋት የተደነገጉትን መርሆዎች እና ደንቦችን በመከተል ጭምር የሚመራ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በዋናነት በ1958ቱ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ የተዘረጉትን ሥነ ሥርዓታዊ መርሆዎችና ደንቦች በመከተል ሊመራና እልባት ሊያገኝ ይገባል።ክርክርን በሕግ የተዘረጋዉን

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ሥነ-ሥርዓት መሰረት በማድረግ መምራት እና መቆጣጠር የፍርድ ቤቶች ኃላፊነት ነዉ፡፡ ፍርድ ቤቶች በሕግ የተዘረጉትን ሥነ ሥርዓታዊ መርሆዎችንና ደንቦችን መሰረት በማድረግ ክርክር የማይመሩና በሥነ ሥርዓት ሕጉ የተጣለባቸዉን ኃላፊነት በአግባቡ የማይወጡ ከሆነ ምክንያታዊ በሆነ አጭር ጊዜ እና ዉስን የሆነ የሰዉና የገንዘብ ሀብት (judicial economy) በመጠቀም ለፍትሐ ብሔር ክርክር እልባት ሊሠጥ እንደሚገባ የሥነ ሥርዓት ሕጉ የሰነቀዉ ዓላማ ሳይሳካ ይቀራል፡፡ በተጨማሪም በዚህ መልኩ ክርክሩን አለመምራት የተከራካሪ ወገኖችን ሥነ ሥርዓታዊ ፍትህ (procedural justice) ከማሳጣት አልፎ ከመሰረታዊ ሕግጋትና ከዉል የተጎናጸፉትን የሥረ-ነገር መብቶች(substantive rights) እንዲያጡ ወደሚያደርግ ድምዳሜ ስለሚያደርስ እንዲህ አይነት አሉታዊ ዉጤት እንዳይመጣ ክርክሮችን በሥነ ሥርዓት ሕጉ የተደነገጉ መርሆዎችንና ደንቦችን በተከተለ መምራት እና እልባት መስጠት ያስፈልጋል፡፡

በሥነ ሥርዓት ሕጉ ከተዘረጉት ሥነ ሥርዓታዊ ደንቦች መካከል አንዱ እና ዋነኛዉ የፍርድ ቤቶችን የዳኝነት ሥልጣን የሚመለከተዉ ሥነ ሥርዓታዊ ደንብ ነዉ፡፡ ከዳኝነት ሥልጣን አይነቶች መካከል አንዱ የሥረ-ነገር ሥልጣን ዳኝነት ሥልጣን ነዉ፡፡ይህ የዳኝነት ሥልጣን በአንድ ሀገር ጉዳዩን ለመዳኘት ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች መካከል የፍርድ ቤቱን የመዳኘት ብቃት ወይም ችሎታ (competence of the court)፣ ፍትሐዊነትን፣ ኢኮኖሚንና የሥራና ሀብት ክፍፍልን መሠረት አድርጎ በገንዘብ ግምት (pecuniary jurisdiction) ወይም በጉዳዩ ዓይነት (subject matter jurisdiction) ወይም ጉዳዩን በመጀመሪያ ሆነ በይግባኝ ደረጃ (original and appellate jurisdiction) የሚያዩት ስለመሆኑ በዋነኛነት ታሳቢ በማድረግ በፍርድ ቤቶች መካከል ስለሚመለከቱት ጉዳዮች አስመልክቶ የሥልጣን ድልድል የሚደረግበት ሥርዓት ነው፡፡

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 9/1 እና 231(1/ለ) መሠረት ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለመመልከት የሥረ-ነገር ዳኝነት ሥልጣን ያለው መሆን አለመሆኑን ለተከሳሽ መጥሪያ ከመላኩና ክርክር ወደ መስማት ሂደት ከመግባቱ በፊት አስቀድሞ የመመርመር ኃላፊነት አለበት፡፡በዚህ የክርክሩ መነሻ ሂደት ላይ ፍርድ ቤቱ የዳኝነት ሥልጣን እንዳለዉ ሳያረጋግጥ ተከሳሹ መከላከያ መልስ እንዲያቀርብ መጥሪያ የላከበት አጋጣሚ ከተፈጠረም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 244(2/ሀ) መሰረት ተከሳሽ ፍርድ ቤቱ ክሱን ለመዳኘት ሥልጣን የለዉም ሲል መቃወም ይችላል፡፡ በዚህ መልኩ ተከሳሽ ወይም ሌላ ተከራካሪ ወገን ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለመዳኘት ሥልጣን የለዉም በሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ሲያነሳ አሊያም የዳኝነት ሥልጣኑ ከሥረ ነገር ዳኝነት ሥልጣን ጋር የተያያዘ ሆኖ ፍርድ ቤቱ ፍርድ ከመስጠቱ በፊት በራሱ አነሳሽነት ጉዳዩን ለመዳኘት የሚያበቃ የሥረ ነገር ዳኝነት ሥልጣን እንደሌለዉ ሲረዳ ተከሳሹ በመከላከያ መልሱ ላይ ያቀረበዉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች እንኳን ቢኖሩ ሌሎች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት የተነሱትን መከራካሪያዎችን መመርመር ሳያስፈልገዉ፣ የፍሬ ነገር ጭብጥ ከመመስረቱና ማስረጃ አስቀርቦ ከመመርመሩ በፊት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 9/2 ፣ 244/1፣245/2 እና 182/3 በተደነገገዉ መሠረት የሥረ ነገር ዳኝነት ሥልጣን የለኝም በማለት መዝገቡን መዝጋት ይኖርበታል፡፡ከዚህ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ጋር በተያያዘ ይህ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 102543(ቅጽ 18) እና በሌሎች መዛግብት ላይ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

ከተያዘዉ ጉዳይ ጋር ተመሳሳይ በሆነና የሱማሌ ክልል የፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሬት ይዞታ ላይ ተፈጠረ የተባለ የሁከት ተግባር ለማስወገድ የቀረበ ክስ በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን ተመልክቶ ዉሳኔ በመስጠቱና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስህተቱን ሳያርም በማለፉ ለዚሁ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 229433 እና 244702 ላይ የሰበር አቤቱታ ቀርቦ ችሎቱም አቤቱታዉን መርምሮ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ በሶማሌ ክልል የፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 152/2008 አንቀጽ 3/1 ስር የተደነገገዉን በሚቃረን አኳኋን የሥረ-ነገር ዳኝነት ሥልጣን ሳይኖረዉ ክሱን ሰምቶ መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት እንደሆነ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሠጥቷል፡፡

ሲጠቃለል የፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በከተማ መሬት ይዞታ ላይ ተፈጠረ የተባለዉን የሁከት ተግባር ለማስወገድ በተጠሪዎች የቀረበዉን ክስ የሚቀርብ ክስ በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን ተቀብሎ ለመዳኘት የስረ-ነገር ዳኝነት ሥልጣን ሳይኖረዉ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን ተቀብሎ መወሰኑም ሆነ ይህንኑ ጉዳዩን በይግባኝ እና በሰበር የተመለከተዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሳያርም መቅረቱ ከላይ በተጠቀሱት መዛግብት ላይ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሚቃረን በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሸ) እና 10(1/ሐ) ስር በተደነገገዉ መሠረት ሊታረም የሚገባዉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ዉሳኔ

1. የሱማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 052-328-214 ላይ በቀን 13/03/2015ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የሱማሌ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 05-1-119/15 ላይ በቀን 29/05/2015 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 05-1-242/15 በቀን 02/09/2015ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 መሠረት ተሽረዋል፡፡

2. የፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሁከት ይወገድልኝ ክስ በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን ተመልክቶ የመወሰን የሥረ-ነገር ሥልጣን የለውም በማለት ወስነናል፡፡ይህ ዉሳኔ ሥልጣን ባለዉ ፍርድ ቤት ክስ ከማቅረብ አያግድም፡፡

3. በዚህ ችሎት የወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡ዉሳኔዉ በቀን 08/02/2017 ተነበበ፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ. 250037

ቀን ፦ ጥቅምት 08 ቀን 2017 ዓ/ም

ዳኞች- እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች፦ ወ/ሮ ሂክማ ሳኒ

ተጠሪዎች፦1.አቶ ሻሎ መካ

2.ወ/ሮ ሃዋ ሂርጳ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ ከአንድ በላይ ጋብቻ ሲፈጸም ንብረት የሚከፋፈልበትን ሥርዓት የሚመለከት ሲሆን የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በሙኔሳ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት በተደረገ ክርክር አመልካች ተከሳሽ 1ኛ ተጠሪ ከሳሽ እና 2ኛ ተጠሪ ደግሞ ጣልቃ ገብ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የአመልካችና 1ኛ ተጠሪ ጋብቻ በፍቺ ከፈረሰ በኋላ ግራቀኙ የንብረት ዝርዝር አቅርበዋል፡፡ በዚህ ችሎት ክርክር እየተደረገበት ያለው አመልካች ባቀረቡት የንብረት ዝርዝር ግምቱ ብር 3000,000 ( ሶስት ሚሊዮን) የሚያወጣ 60 ቆርቆሮ መጋዘን እና 60 ሎክ ቆርቆሮ መኖሪያ ቤት ፣በ100 ካ.ሜ ላይ የሚገኝ አዋሳኞቹ በክሱ የተገለጸ በቀርሳ ከተማ ቀበሌ 02 ውስጥ የሚገኝ ቦታ፣ ቀርሳ ከተማ ውስጥ የሚገኝ አዋሳኞቹ በክሱ የተገለጸ ግምቱ ብር 3,000,000 ( ሶስት ሚሊዮን ) የሚያወጣ 170 ካ.ሜ ቦታ ፣ 500 ካ.ሜ የሆነ በቀርሳ ከተማ ቀበሌ 02 ውስጥ የሚገኝ አዋሳኞቹ በክሱ የተገለጸ ግምቱ ብር 2,000,000 ( ሁለት ሚሊዮን) የሚያወጣ ቦታ ፣ በ120 ካ.ሜ ላይ የሚገኝ በቀርሳ ከተማ ቀበሌ 01 ውስጥ የሚገኝ አዋሳኞቹ በክሱ የተገለጸ ግምቱ ብር 2,000,000 ( ሁለት ሚሊዮን ) የሚያወጣ የንግድ ቤት ፣ 9 ሜትር የሆነ ቀበርሳ ከተማ ቀበሌ 01 ውስጥ የሚገኝ አዋሳኞች በክሱ |የተገለጸ ግምቱ ብር 600,000 ( ስድስት መቶ ሺህ ) የሚያወጣ ገበያ፣ እና ሌሎች ንብረቶችን በጋብቻ ወቅት ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በጋራ ያፈራናቸው ንብረቶች ስለሆኑ ድርሻዬ እንዲያካፈለኝ እንዲወሰን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

1ኛ ተጠሪ በሰጡት መልስ ከአመልካች ጋር ጋብቻ የፈጸምነው በ20/01/2010 ዓ/ም ነው፣ 2ኛ ተጠሪ ቀድሞ ያገባኋት ሚስቴ ናት፣ ንብረቱ አስቀድሞ የተፈራው ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ስለሆነ አመልካችን አይመለከትም በማለት ተከራክረዋል፡፡ 2ኛ ተጠሪ ጣልቃ በመግባት ባቀረቡት አቤቱታ 1000 ካ.ሜትር ቦታ ላይ የሚገኝ አዋሳኞቹ በአቤቱታው የተገለጸ 60 ሉክ ቆርቆሮ መጋዘን እና 60 ሉክ ቆርቆሮ መኖሪያ ቤት ከባለቤቴ ጋር በ1996 ውስጥ የሰራነው ነው፣ 6 በር ያለው 170 ካ.ሜትር በቀርሳ ከተማ ውስጥ የሚገኝ አዋሳኞቹ በአቤቱታው የተገለጸ ግምቱ ብር 200,000 ( ሁለት መቶ ሺህ ) የሚያወጣ በስሜ ተመዝግቦ የሚገኝ እና የግሌ አመልካች ተጠሪን ከማግባቷ በፊት በ2011 ዓ.ም የገዛሁት ነው ፣ 8 በር ቤት 500 ካ.ሜትር ላይ ቀርሳ ከተማ ቀበሌ 02 ውስጥ የሚገኝ አዋሳኞቹ በአቤቱታው የተገለጸ ግምቱ ብር 300,000 ( ሶስት መቶ ሺህ ) የሚያወጣ በስሜ ተመዝግቦ የሚገኝ በ 2009 ዓ.ም በግዢ ያገኘሁት የግል ንብረቴ ነው፣ 5 በር 120 ካ.ሜትር ላይ የሚገኝ በቀርሳ ከተማ ቀበሌ 01 ውስጥ የሚገኝ አዋሳኞቹ በአቤቱታው የተገለጸ ግምቱ ብር 100,000 ( አንድ መቶ ሺህ ) የሚያወጣ የንግድ ቤት ከባለቤቴ ጋር በ2005 ዓ.ም የገዛነው ነው፣ ስለሆነ ንብረቶቹ ከክሱ ወጥተው እንዲወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

1ኛ ተጠሪ 2ኛ ተጠሪ ባቀረቡት የጣልቃ ገብ አቤቱታ ላይ በሰጡት መልስ 2ኛ ተጠሪ ግምታቸውንና ዝርዝራቸውን በመጥቀስ ዘርዝራ ያቀረበቻቸው ንብረቶች ከክሱ ቢወጣላት አልቃወምም በማለት የተከራከሩ ሲሆን አመልካች በሰጡት መልስ 2ኛ ተጠሪ 1ኛ በተራ ቁጥር የገለጸችው ቤት ሌላ መሬት ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ገዝተን አዲስ ቤትም ሰራን እንጂ የ2ኛ ተጠሪ የግሏ አይደለም፣ 170 ካ.ሜትር ላይ የሚገኘው 6 በር ቤት እኔ እና 1ኛ ተጠሪ በ 2009 ዓ.ም ከተጋባን በኋላ በ2011 ዓ.ም የገዛነው የጋራ ንብረት ነው እንጂ የ2ኛ ተጠሪ የግል ንብረት አይደለም ፣ በተራ ቁጥር 3 ላይ 2ኛ ተጠሪ የገለጸችው ቤት በጋብቻ ውስጥ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ያፈራነው የጋራ ንብረት እንጂ የሷ አይደለም ፣በተራ ቁጥር 4 ላይ 2ኛ ተጠሪ የገለጸችው ቤት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በጋብቻ ውስጥ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ስንነግድበት የነበረ በጋራ ገዝተን እስካሁን ድረስ በኔ እጅ የሚገኝ የአመልካችና እና የ1ኛ ተጠሪ ነዉ በማለት መልስ ሰጥተዋል

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር፣የምስክሮች ቃልና ከሚመለከተው የመንግስት አካል የቀረቡ ማስረጃዎችን አግባብነት ካለው ህግ ጋር በመመርመር በኦሮሚያ የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 117 መሰረት ባልና ሚስት በጋብቻ ውስጥ ያፈሩት ንብረት ጋብቻቸው ሲፈርስ እኩል መካፈል እንዳለበት የሚደነግግ በመሆኑና ባል ወይንም ሚስት ንብረቱ የግላቸው መሆኑን በማስረዳት የግል ንብረታቸውን መልሰው መውሰድ እንደሚችሉ እንዲሁም አንቀጽ 73 መሰረት ባልና ሚስት ጋብቻ ሲፈጽሙ በግል ያላቸውን ንብረት የግላቸው ሆኖ እንደሚቀር የሚደነግግ በመሆኑ  አዋሳኞቹ በምስራቅ መንገድ ፣ በምእራብ ነጃ ኡስማን ፣ በሰሜን ጌቱ ጥላሁን እና በደቡብ መንገድ መካከል የሆነ 105 ካ.ሜትር ላይ የሚገኘው 40 ሉክ ቆርቆሮ መኖሪያ ቤት በአመልካች ስም ተመዝግቦ ያለ ግምቱ ብር 350,000.00 የሚያወጣ አመልካችና ተጠሪ በጋብቻ ውስጥ ያፈሩት ንብረት መሆኑን በሰው ምስክር እና በጽሁፍ ማስረጃ የተረጋገጠ ስለሆነ  እኩል እንዲካፈሉ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል ። እንዲሁም ቀርሳ ከተማ ቀበሌ 02 ውስጥ የሚገኝ አዋሳኞቹ በምስራቅ መንገድ ፣ በምእራብ መገርሳ ዲባባ ፣ በሰሜን የመንግስት ቤት እና በደቡብ ዩሱፍ ናሲር 6 በር የሆነ 170 ካ.ሜትር ቤት እና ቀርሳ ከተማ ቀበሌ 02 ውስጥ የሚገኝ 500 ካ.ሜትር ላይ ያለ አዋሳኞቹ በምስራቅ መንገድ ፣ በምእራብ ሀጂ አማን ገመዳ ፣ በሰሜን ብርሃኑ ብሩ እና በደቡብ መንገድ መካከል የሚገኘው 8 በር ቤት 2ኛ ተጠሪ የገዛችው ንብረት መሆኑ በጽሁፍ ማስረጃ እና በሰው ምስክር የተረጋገጠ ስለሆነ የ2ኛ ተጠሪ ንብረት ነው በማለት ተወስኗል። ፍርድ ቤቱ ለዚህ ሰበር ምክንያት ባልሆኑ ሌሎች ጉዳዮች ላይም ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ አስተላልፏል።

አመልካች ይህንን ውሳኔ በመቃወም በየደረጃው ላሉ ፍርድ ቤቶች ቅሬታ ቢያቀርቡም ውሳኔው ሳይቀየር ቀርቷል።

አመልካች ሰኔ 29 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይህን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ሲሆን ይዘቱም፡- አመልካችና 1ኛ ተጠሪ በህዳር ወር 2009 ዓም ተጋብተን በቀን 15/03/2015 ዓ.ም የፍቺ ዉሳኔ እስከተሰጠ ጊዜ ድረስ በባልና ሚስትነት ልጆችና ንብረት አብረን ያፈራን ሲሆን 2ኛ ተጠሪም የ1ኛ ተጠሪ ባለቤት በመሆን አብረን ኖረናል ፣አመልካችና 2ኛ ተጠሪም ሁለታችንም የ1ኛ ተጠሪ ሚስቶች አብረን ባደረግነዉ ጥረት ስድስት ሰርቪሶች ያሉት በ170 ካ.ሜ. ላይ የሰፈረዉን መኖሪያ ቤት በቀርሳ ከተማ ቀበሌ 02 ዉስጥ በ 2011 ዓ.ም በተደረገዉ የግዢና ሽያጭ ዉል በ2ኛ ተጠሪ ሥም ተገዝቷል፣እንደሁም ስምንት ሰርቪሶች ያሉት በ 500 ካ.ሜ. የመሬት ስፋት ላይ የሰፈረዉን መኖሪያ ቤት በቀርሳ ከተማ ቀበሌ 02 ዉስጥ በ 2009 ዓም አመልካችና 1ኛ ተጠሪ በትዳር እያለን በተደረገዉ የግዢና ሽያጭ ዉል እስከተገዛ ድረስ የጋራ ንብረት መሆኑን በህግ ግምት የሚወሰድበት ሆኖ እያለ የ2ኛ ተጠሪ የግል ንብረት እንደሆነ መቆጠሩ ተገቢ አይደለም፣ የክርክሩ መነሻ የአመልካችና እና 1ኛ ተጠሪ መሃከል የተደረገ በባልና ሚስት ክርክር መሆኑ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

እያታወቀ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት  ክርክሩ ከባልና ሚስት ንብረት ክርክር ዉጪ እንደሆነ አደርጎ መዉሰዱ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ፣ ቤቶቹ በ2ኛ ተጠሪ ሥም በመመዝገቡ ንብረቱ 3 ቦታ አይካፈልም እንኳን ቢባል አመልካች የባሌን ድርሻ እንድካፈል አለመወሰኑ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፣ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የሰበር ሰሚው ችሎትም የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ 1ኛ ተጠሪ የአመልካች እና የ2ኛ ተጠሪ ባለቤት የነበሩ መሆኑ ፣ በ2ኛ ተጠሪ ስም የተመዘገቡ ክርክር ያስነሱ ንብረቶች የአመልካች ጋብቻ ጸንቶ እያለ የተፈሩ እስከሆነ ድረስ አመልካች በንብረቶች ላይ መብት የላቸውም መባሉ የኦሮሚያ የቤተሰብ ሕግ ሆነ የኢፌዴሪ ሕገ - መንግስት አንቀጽ 40 ላይ የተመለከተን የንብረት መብታቸውን ያከበረ መሆን አለመሆኑን ሊመረመር የሚገባው በመሆኑ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ታዟል፡፡

ተጠሪዎች ሰኔ 18 ቀን 2016 ዓ.ም የሰጡት መልስ ይዘት፡- 1ኛ ተጠሪ ከአመልካች ጋር ጋብቻ የፈጸምኩት ሰኔ 30 ቀን 2010 ዓ.ም ሲሆን ከሷ ጋር ያፈራሁት በ105 ካ.ሜ ላይ ያረፈ 40 ቆርቆሮ ቤት ነው፣ በቀርሳ ከተማ ውስጥ ያለውና 6 ክፍል ስርቪስ ቤት የተገዛው በ 2011 ዓ.ም በ2ኛ ተጠሪ ስም ሲሆን ከአመልካች ጋር ጋብቻ በፈጸምን በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ይህን ያህል ቤት የሚሠራ ንብረት አላፈራንም፣ በቀርሳ ከተማ በ 5000 ካ.ሜ ላይ ያለውን ቤት 1ኛ ተጠሪ  አመልካችን ከማግባቱ በፊት በቀን 05/10/2009 በተጻፈ የሽያጭ ውል የገዛሁት የግል ንብረቴ ነው፣በ1000 ካሬ ሜትር መሬት ላይ ያለውን ቤት በ1998 ዓ.ም ከ 2ኛ ተጠሪ ጋር አብረን እያለን የገዛነው ስለሆነ አመልካችዋን አይመለከትም ፣በ120 ካ.ሜ ላይ ያሉ 5 ክፍል ቤቶች ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በ 2008 ዓ.ም በጋራ ገዝተን የምንጠቀምበት እንጂ አመልካችን የሚመለከት አይደለም፣የገበያ መደብ በ2000 ዓ.ም የያዝኩት የመንግስት ንብረት ነው፡፡በመሆኑም የአመልካች አቤቱታ የህግ መሰረት የሌለው በመሆኑ ውድቅ ተደርጎ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ህጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

እንደመረመርነው ጉዳዩ የአመልካችና የ1ኛ ተጠሪ ጋብቻ በፍቺ ቀሪ ከሆነ በኋላ የቀረበ የንብረት ክፍፍል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን በዚህ ችሎት ዋናው የክርክር ጭብጥ ክርክር ያስነሱት በቀርሳ ከተማ ቀበሌ 02 ውስጥ በ170 ካሬ ሜትር ይዞታ ላይ የሚገኝ ስድስት በር ቤት እና በቀርሳ ከተማ ቀበሌ 02 ውስጥ በ500 ካሬ ሜትር ይዞታ ላይ የሚገኝ ስምንት በር ቤት 1ኛ ተጠሪ ከአመልካች ጋር ጋብቻ ሳይፈጸሙ አስቀድመው ያፈሩት ንብረት ነው ወይስ ከአመልካች ጋር ጋብቻ ከፈጸሙ በኋላ የተፈራ የጋራ ንብረት ነው የሚለው ነው፡፡ ክርክሩን በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሰረት መምራት እና መቆጣጠር የፍርድ ቤቱ ኃላፊነት ሲሆን በተገቢው ሁኔታ ካልተመራ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ዓላማዎች የሆኑትን እንደ አንጻራዊ እውነትን

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የመፈለግ፣ ሥነ-ሥርዓታዊ ፍትህ፣ ክርክርን ውጤታማ፣ ወጭና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ መምራት የመሳሰሉትን ማሳካት ስለማይቻል የተከራካሪዎችን መብት ይነካል። ክርክር የሚወሰነው በተጠየቀው ዳኝነት አግባብ እንደሆነ የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 182(2) ላይ ተመልክቷል። ፍርድ ቤቱም ከቀረበው ዳኝነት አኳያ ከግራቀኙ ክርክር በመነሳት በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 246 እና ተከታዮቹ መሠረት በተነሱት ጉዳዮች ጭብጥ መስርቶ ውሳኔ የመስጠት ኃላፊነት አለበት። በክርክር አመራር ሥርዓት ሂደቱ የግራቀኙ ንብረት ክፍፍል እና የሀብት ማጣራት ስራ ሲከናወን በቤተሰብ ሕጉ ስለሀብት ስለሚጣራበት ሁኔታ የተዘረጋውን ሥርዓት ግምት ውስጥ ማስገባት ይገባል።

የኦሮሚያ ክልል የቤተሰብ ሕግ የሆነውን አዋጅ ቁጥር 69/1995 አንጽ 78 መሠረት ባልናሚስት ከተጋቡ በኂላ ያፈሯቸው ንብረቶች በሙሉ የጋራ ሀብት እንደሚሆኑ ተመልክቷል። በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 73 እና 74 መሠረት የግል ንብረት የሚሆነው ከጋብቻ በፊት የተፈራ ንብረት፣ ከጋብቻ በኂላ አንደኛው ተጋቢ በውርስ ወይም በስጦታ ያገኘው ንብረት እና የግል ንብረት የሆነው ሲለወጥ /ለውጡም በፍርድ ቤት ሲጸድቅ/ ስለመሆኑ በዝርዝር ተመልክቷል። ጋብቻ ሲፈርስ በኦሮሚያ

የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 112 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ስለሀብት ማጣራት የተመለከቱ ተፈጻሚነት አላቸው፤ ንብረቱ የተፈራው በጋብቻ ውስጥ በነበረ ግንኙነት ወይስ ከጋብቻ በፊት የሚለው የፍሬ ነገር ጭብጥ ነው፤ በክርክር ሂደት ፍሬ ነገሮችን ማረጋገጥ የሚቻልባቸው ዘዴዎች ማስረጃ፣ በፍርድ ቤት በሚሠጥ የእምነት ቃል፣ ፍርድ ቤት በራሱ ግንዛቤ ሊወስድባቸው የሚችሉ ጉዳዮች፣ የሕግ ግምት እና የመሓላ ቃል ናቸው። በፍትሐ ብሔር ክርክር የምንከተለው የማስረዳት ደረጃ ከሁለቱ ወገን የተሻለ ያስረዳው ማን ነው (preponderance of evidence) የሚለውን በመመርመር ነው፤የማስረጃ ተገቢነት፣ የማስረጃው ተቀባይነትን ደንቦችን መከተል እና ለማስረጃው የሚሰጠውን ክብደት በመለየት የመወሰን ኃላፊነት ማስረጃ ለመስማትና ለመመዘን ኃላፊነት ያለባቸው ፍርድ ቤቶች ዋና ተግባር ነው።

ማስረጃ ለመመዘን ሥልጣን የተሠጠው ፍርድ ቤት ማስረጃ ሲቀበል የተከራካሪዎችን እኩል የመደመጥ መብት ካላከበረ፣ የማስረዳት ሸክም (burden of production) የማን ነው የሚለውን ካልለየ፣ የማስረጃ ተቀባይነትና ተገቢነት ላይ መከተል የሚገባውን ሥርዓት ካልተከተለ፣ በምዘና ጊዜ የሁሉንም ተከራካሪዎች ማስረጃ አብሮ ካልመዘነ፣ ከማስረዳት ደረጃ (standard of proof) አንጻር በሚጠይቀው ደረጃ ልክ መረጋገጡን ካላሳየ እና በመሠረታዊ ሕግ ሆነ በሥነ-ሥርዓት ሕግ ያሉትን የማስረጃ ሕጎችና መርሆች ካላከበረ ጉዳዩ የማስረጃ ምዘና ሳይሆን የሕግ አተረጓጎም ስህተትና ፍርድ ቤት ያለበትን ኃላፊነት አለመወጣት ስለሚሆን የሰበር ሰሚ ችሎቱ የሚመለከተው ጉዳይ ስለመሆኑ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 172206 እና ሌሎች በርካታ መዝገቦች ላይ አስገዳጅ ትርጉም የተሰጠበት ነው።

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በተያዘው ጉዳይ አመልካች ዳኝነት የጠየቁባቸውን ቤቶች በተመለከተ የግራ ቀኙን ክርክር የሰሙ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ የሚከራከሩት ከአመልካች ጋር ጋብቻ የፈጸምነው በ20/01/2010 ዓ/ም ሲሆን ከ2ኛ ተጠሪ የቀደመ ጋብቻ አለን፣ ንብረቱም የተፈራው ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በማለት ነው፡፡ 2ኛ ተጠሪም በክርክሩ ጣልቃ በመግባት ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ጋብቻ ያላቸው ስለመሆኑና ክርክር ያስነሱት ቤቶች አመልካች ከመገባታቸው በፊት በግዥ የተፈሩ ንብረቶች ናቸው፣ አመልካችን አይመለከትም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በበኩላቸው ጋብቻ የተፈጸመው በ2009 ዓ/ም ነው፣ ንብረቶች በጋብቻ ውስጥ የተፈሩ ስለሆነ ልካፈል ይገባል ብለዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶች የግራቀኙን ማስረጃ በመስማት በቀርሳ ከተማ ቀበሌ 02 ውስጥ በ170 ካሬ ሜትር ይዞታ ላይ የሚገኝ ስድስት በር ቤት እና በቀርሳ ከተማ ቀበሌ 02 ውስጥ በ500 ካሬ ሜትር ይዞታ ላይ የሚገኝ ስምንት በር ቤት 1ኛ ተጠሪ ከአመልካች ጋር ጋብቻ ከመፈጸማቸው በፊት የተፈሩ ናቸው፣ 2ኛ ተጠሪም ቤቶቹን ገዝተው መብት ያገኙበት ስለሆነ አመልካች ሊካፈሉ አይገባም በማለት ወስነዋል፡፡

በኦሮሚያ የቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 79/1/ መሠረት አንደኛው ወገን ንብረቱ የግል መሆኑን ካላስረዳ በስተቀር ንብረቶች የጋራ ንብረት እንደሆኑ ግምት የሚወሰድባቸው ስለመሆኑ ይደነግጋል፡፡ ይሕም በቀርሳ ከተማ የሚገኙ ቤቶች የጋራ ንብረት እንደሆነ የሕግ ግምት እንደተወሰደበት የሚያረጋግጥ ነው፡፡ የሕግ ግምት ፍሬ ነገርን ከማረጋገጫ ዘዴዎች አንዱ በመሆኑ በሕግ ግምቱ ተጠቃሚ የሆነ ሰው ንበረቱ የጋራ ስለመሆኑ ቅድሚያ የማስረዳት ሸክም ሊጣልበት አይችልም፤ የሕግ ግምቱ ንብረቱ የጋራ እንደሆነ ግምት የሚወሰድ በመሆኑና የሕግ ግምቱ በተቃራኒ ማስረጃ እስካልተስተባበለ ድረስ ሕጋዊ ውጤት ያለው ነው፤ 1ኛ ተጠሪ የሕግ ግምቱን እንዲያስተባብሉ ቅድሚያ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ተደርጎ የሕግ ግምቱን የሚያስተባብልና ንብረቱ አስቀድሞ የተፈራ የግል ሀብት መሆኑን ካስረዱ አመልካች ይህን ማስረጃ እንዲያስተባብሉ ያላቸውን ማስረጃ በመመዘን መወሰን የሚገባው ስለመሆኑ ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 248963 ከሰጠው ትርጉም መረዳት ይቻላል፡፡

የሥር ፍርድ ቤቶች ንብረቶቹ የተፈሩት በጋብቻ ውስጥ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ከመወሰናቸው በፊት የጋብቻ ጊዜው አከራካሪ ሲሆን አስቀድመው ጋብቻው መቼ እንደተፈጸመ የማጣራትና የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ አመልካች ጋብቻው የተፈጸመው በ2009 ዓ/ም ነው በሚል የገለጹ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ በበኩላቸው ከአመልካች ጋር ጋብቻ የተፈጸመው በ20/01/2010 ዓ/ም ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ በቀርሳ ከተማ ቀበሌ 02 ውስጥ በ500 ካሬ ሜትር ይዞታ ላይ የሚገኝ ስምንት በር ቤት በሰኔ 05 ቀን 2009 ዓ/ም የተገዛ ስለመሆኑ በተጠሪዎች ክርክር የቀረበ በመሆኑ ንብረቱ የጋራ መሆን አለመሆኑን ለመወሰን አመልካች ጋብቻ የፈጸሙበት ጊዜን ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ የጋብቻ ጊዜው ሳይጣራ ንብረቱ አስቀድሞ የተፈራ ነው ሲሉ የሥር ፍርድ ቤቶች የደረሱበት መደምደሚያ ስህተት ያለበት ነው፡፡

በሌላ በኩል በቀርሳ ከተማ ቀበሌ 02 ውስጥ በ170 ካሬ ሜትር ይዞታ ላይ የሚገኝ ስድስት በር ቤት በ2011 ዓ/ም የተገዛ ስለመሆኑ በተጠሪዎችም የታመነ ፍሬ ነገር ነው፣ 1ኛ ተጠሪ ጋብቻው ተፈጸመ በሚል

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የገለጹትን ጥቅምት 20 ቀን 2010 ዓ/ም መነሻ ቢደረግ እንኳን ንብረቱ 2011 ዓ/ም አመልካች ጋር ጋብቻ ከፈጸሙ በኋላ የተፈራ ስለመሆኑ ያረጋግጣል፡፡ በጋብቻ ውስጥ ከተፈራ ደግሞ ንብረቱ የአመልካችም የጋራ ሀብት እንደሆነ የሚወሰድ ነው፡፡ ንብረቱ 1ኛ ተጠሪ ካላቸው የመጀመሪያ ጋብቻ ውስጥ መፈራቱ ብቻውን ንብረቱ ላይ በሁለተኛ ጋብቻ የፈጸሙትን አመልካችን መብት እንዳይኖራቸው የሚያደርግ አይደለም፡፡ የቤት ሽያጭ ውሉ በመጀመሪያ ጋብቻ የፈጸሙት 2ኛ ተጠሪ ስም መደረጉ ንብረቱ ሁለተኛው ጋብቻ ከተፈጸመ በኋላ እስከተፈራ ድረስ አመልካች በሕጉ የተሰጣቸውን የጋራ ሀብት ተጠቃሚነት አያስቀርም፡፡ 2ኛ ተጠሪ በንብረቱ መፈራት የተለየ አስተዋጽኦ ካላቸው ይሕ ፍሬ ነገር ተጣርቶ የድርሻ ክፍፍሉ ላይ ልዩነት በመፍጠር መወሰን የሚቻልበት ስርዓት ስለመኖሩ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 45548 /በቅጽ 13 እንደታተመ/ አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ንብረቱ በመፈራት ረገድ ተጋቢዎች ያላቸው ልዩ አስተዋጽኦ ክርክር ተደርጎበት በማስረጃ ከተጣራ በኋላ ተከራካሪዎች ያላቸው ድርሻ ተለይቶ ሊወሰን ሲገባ አመልካች ጋብቻ ከፈጸሙ በኋላ መፈራቱ የተረጋገጠው ቤት ላይ ምንም መብት የላቸውም ተብሎ መወሰኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 431077 ሰኔ 13 ቀን 2015 ዓ/ም፣ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 416632 ሚያዚያ 18 ቀን 2015 ዓ/ም፣ የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 130245 የካቲት 03 ቀን 2015 ዓ/ም እና የሙኔሳ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 44255 ታህሳስ 20 ቀን 2015 ዓ/ም የሰጡት ውሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1)(ለ) መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2. በቀርሳ ከተማ ቀበሌ 02 ውስጥ በ170 ካሬ ሜትር ይዞታ ላይ የሚገኝ ስድስት በር ቤት እና በቀርሳ ከተማ ቀበሌ 02 ውስጥ በ500 ካሬ ሜትር ይዞታ ላይ የሚገኝ ስምንት በር ቤት ላይ የተሰጠው ውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡ ቀሪው የውሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡

3. የሙኔሳ ወረዳ ፍርድ ቤት በውሳኔ የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር መቼ ጋብቻ እንደፈጸሙ በማጣራት በቀርሳ ከተማ ቀበሌ 02 ውስጥ በ500 ካሬ ሜትር ይዞታ ላይ የሚገኝ ስምንት በር ቤት ላይ አመልካች ያላቸውን መብት እንዲወሰን፣ ንብረቱ የተፈራው አመልካች ጋብቻ ከፈጸሙ በኋላ ከሆነ ንብረቱ በመፈራት ረገድ ግራቀኙ ያላቸውን አስተዋጽኦ በመለየት ድርሻቸውን እንዲወሰን፤

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በቀርሳ ከተማ ቀበሌ 02 ውስጥ በ170 ካሬ ሜትር ይዞታ ላይ የሚገኝ ስድስት በር ቤት አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ጋብቻ ከፈጸሙ በኋላ የተፈራ በመሆኑ አመልካች ድርሻ መብት ይኖራቸዋል፣ ነገር ግን ድርሻ ክፍፍል መጠኑ ምን ያሕል ነው የሚለውን በተመለከተ ንብረቱ በመፈራት ረገድ ግራቀኙ ያላቸውን አስተዋጽኦ በማጣራት እንዲወሰን በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(2) መሠረት ጉዳዩን መልሠናል፡፡

4. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡ የሙኔሳ ወረዳ ፍርድ ቤት በውሳኔው መሠረት እንዲፈጽም አዘናል፡፡ ይጻፍ
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የሰ/መ/ቁጥር---250125

ቀን- ጥቅምት 06 ቀን 2017 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ብርሃኑ መንግስቱ

ማርታ ተካ

**አመልካች**: - ወ/ሮ መስቲካ ለገሰ

**ተጠሪዎች፡-** 1. የጭሮ ከተማ አስተዳደር ማዘጋጃ ቤት

2. የጨፌ አራራ ቀበሌ 01 አስተዳደር ጽ/ቤት

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው በከተማ ይዞታ ላይ ካርታ እንዲሰጥ የቀረበ የዳኝነት ጥያቄን የተመለከተ ጉዳይ ሲሆን የተጀመረው በጭሮ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍ/ቤት አመልካች ከሳሽ ሲሆኑ የጭሮ ከተማ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ተከሳሽ እንዲሁም የአሁን ተጠሪዎች ጣልቃ ገቦች ነበሩ፡፡ የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ የምዕራብ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 62518 ግንቦት 25 ቀን 2014 ዓ.ም የወረዳዉን ፍ/ቤት ዉሳኔ በመሻር ተሰጥቶ በየደረጃዉ ባሉ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ችሎቶች የጸናዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በሚል ነዉ፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አመልካች በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ:- አመልካች አባታቸዉ አቶ ለገሰ ደረሰ በ1967 ዓ.ም በቁኒ ከተማ ቀበሌ 01 ዉስጥ ከሚገኝ ቤት ጋር ተመጣጣኝ በመሆኑ በተፈጸመ ልዋጭ ያገኙትና የግል ንብረታቸዉ የሆነ ቢላል ሬስቶራንት ተብሎ የሚታወቅ በጭሮ ከተማ ጨፌ አራራ ቀበሌ 01 ዉስጥ በ500 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ የሚገኝ አዋሳኞቹ በክሱ የተገለጸዉን ሆቴል ንግድ ቤት ያለ ምንም ተቃዉሞ ሲጠቀሙበት ቆይተዋል፡፡ የአመልካች አባት በ2001 ዓ.ም እንዲሁም እናታቸዉ በ2014 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸዉ ንብረቱ ተላልፎላቸዉ የከተማ መሬት ደንብና አዋጅን በማይጥስ መንገድና መስፈርት ተሟልቶ የድሮ የቦታ ይዞታ ማረጋገጫ ማስረጃ ሊሰጥ የቻለ ሆኖ ሳለ ለስር ተከሳሽ በተለያዩ ጊዜ ጥያቄ ቢያቀርቡም ያለ በቂ እና አሳማኝ ማስረጃ ፈቃደኛ አለመሆኑን ገልጸዉ በግል ንብረታቸዉ ላይ ካርታ እንዲሰጣቸዉ እንዲወሰን ጠይቀዋል፡፡

የስር ተከሳሽ ለክሱ በሰጠዉ መልስ፡- በአመልካች ጥያቄ መሠረት ካርታ ከመሰጠቱ በፊት ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 47/97 የተወረሰ መሆን አለመሆኑ መረጋገጥ ስለነበረበት የከተማዉ ማዘጋጃ ቤት አገልግሎት ጽ/ቤት እና ለጨፌ አራራ ቀበሌ አስተዳደር ጥያቄ አቅርቦ ቤቱ የተወረሰና በልዋጭ የተያዘ በመሆኑ ካርታ እንዳይሰጥበት በደብዳቤ ቅሬታ በማቅረባቸዉ ሳይሰጥ ቀርቷል፡፡ ስለሆነም በመንግስት ቤት ላይ ለአመልካች ካርታ አንሰጥም ማለታቸዉ ተገቢ መሆኑና ማዘጋጃ ቤቱና ቀበሌዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 43 መሠረት ወደ ክርክሩ እንዲገቡ እንዲደረግ በመጠየቅ ተከራክሯል፡፡

የአሁን ተጠሪዎች ወደ ክርክሩ ጣልቃ እንዲገቡ ተደርጎ በሰጡት መልስ ክርክር ያስነሳዉ ቤት ንብረትነት የአመልካች ሳይሆን በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት የቤቱ ባለንብረት ከሆኑት አቶ ወልዱ መንገሻ እና ወ/ሮ ንጋቷ አየለ በመንግስት የተወረሰ ቤት በመሆኑ ለግለሰብ ካርታ የማይሰጥበት እና በዉርስ ሊተላለፍ የማይችል ነዉ፡፡ አመልካች በቁኒ ከተማ በሚገኘዉ ቤት ልዋጭ አገኘሁት የሚሉትን አስልክቶ ከመንግስት አካል የልዋጭ ዉል አላቀረቡም፡፡ አመልካች ከፈለጉ በቁኒ ከተማ በሚገኘዉ ቤት ላይ መብት ማስመለስ ይገባቸዋል እንጂ የአመልካች አባት በአደራ እንዲኖሩበት የተባለዉን ቤት ለመጠየቅ መብት የላቸዉም፡፡ ያቀረቡት የግብር ደረሰኝ በየትኛዉ ቤት ላይ እንደተከፈለ አይለይም፡፡ ሌላዉ ማስረጃ ቃለ ጉባኤ፣ የኪራይ ዉል እና የባለንብረትነት ዉሳኔ የማይገናኝ በመሆኑ ክሱ ዉድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የጭሮ ወረዳ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃዎች ሰምቶ፣ አጣርቶና መርምሮ፡- ክርክር ባስነሳዉ ቤት ላይ አመልካች ካርታ ወይም የይዞታ ማረጋገጫ ማስረጃ ለማግኘት በአዋጅ ቁጥር 47/67 አንቀጽ 14(3) እና በክልሉ አዋጅ ቁጥር 230/2013 አንቀጽ 49(2) መሠረት የአመልካች አባት ቤቱን በልዋጭ መያዛቸዉን በሰነድ ማስረጃ አስረድተዉ ባሉበትና አመልካች ክርክር ባስነሳዉ ቤትና በቁኒ ከተማ ከሚገኘዉ ቤት መካከል በመረጠችዉ ላይ ካርታ ወይም የይዞታ ማረጋገጫ ማስረጃ የማግኘት መብት ያላቸዉ በመሆኑ ካርታ ሊሰጣቸዉ እየተገባ የስር ተከሳሽ የተጠሪዎችን ክርክር ምክንያት በማድረግ መከልከሉ ተገቢ አይደለም፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ክርክር ባስነሳዉ ቤት ላይ ለአመልካች ካርታ ወይም የይዞታ ማረጋገጫ ይሰጣቸዉ በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝተዉ ተጠሪዎች ባቀረቡት ይግባኝ መነሻነት ጉዳዩን የተመለከተዉ የምዕራብ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ መርምሮ የአመልካች አባት ክርክር ያስነሳዉን ቤት በልዋጭ ስለማግኘቱ በተጨባጭ ማስረጃ አልተረጋገጠም፡፡ የልዋጭ ዉል መፈጸሙ እስካልተረጋገጠ ድረስ በአዋጁ መሠረት በተወረሰ ቤት ላይ ካርታ ሊሰጣቸዉ አይገባም በማለት የወረዳዉን ፍ/ቤት ዉሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡ በዚህ ዉሳኔ ባለመስማማት አመልካች ባቀቡት ይግባኝ መነሻነት ጉዳዩን የተመለከተዉ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙን አከራክሮና መርምሮ አመልካች ክርክር ባስነሳዉ ቤት ላይ የባለንብረትነት ዝዉዉር ከመንግስት ጋር መደረጉን አግባብነት ባለዉ ማስረጃ ያላረጋገጡና የቤት ለዉጡ በአዋጅ ቁጥር 47/67 አንቀጽ 16(6) መሠረት ከሆነ ደግሞ በአዋጁ ድንጋጌ መሠረት በአደራ ሰጥተዉ የነበሩትን ቤት ከሆነ ያንን አካል መጠየቅ ይኖርባቸዋል እንጂ በክሱ አግባብ ሊጠይቁ አይችሉም በማለት የዞኑን ከፍተኛ ፍ/ቤት ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ በመቀጠል አመልካች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ሰበር ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘት፡- የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 69208 እና 106535 በጽሁፍ የተደረገ ስምምነት ከጠፋ ሰነዱ የጠፋ መሆኑን፤ ስምምነቱ የተፈጸመ እና የስምምነቱም ቃል ምን እንደሆነ ስምምነቱ ሲፈጸም በነበሩ ምስክሮች ለማስረዳት እንደሚቻል የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1730 እና 2003 ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ የወረዳዉ ፍ/ቤት አመልካች ባቀረቧቸዉ የሰዉ እና የሰነድ ማስረጃዎች የለዉጥ ስምምነቱ በ1970 ዓ.ም መደረጉን እና በተጠሪዎች እጅ እያለ በ1983 ዓ.ም የመንግስት ለዉጥ ሲደረግ በመቃጠሉ መጥፋቱን፤ እንዲሁም የስምምነቱን ይዘት፤ ስምምነቱን በፈጸሙት እና ቃለ-ጉባኤዉን የያዙትን ኮሚቴዎች አቅርበዉ በሚገባ አስረድተዋል፡፡ ሆኖም የስር ፍ/ቤቶች ዋናዉ የስምምነቱ ሰነድ ካልቀረበ በስተቀር ስምምነቱ ስለመኖሩ ስምምነቱን ባስፈጸሙት እና በጸፉት ምስክሮች ማስረዳት አይቻልም በማለት የሰጡት ዉሳኔ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 2003፣ 1730(1) ድንጋጌዎች እና የሰበር አስገዳጅ ትርጉም የሚቃረን በመሆኑ ሊሻር ይገባል፡፡

ይግባኝ ሰሚ ችሎቶች ተጠሪዎች በስር ፍ/ቤት አንስተዉ ያልተከራከሩበትን ነጥብ በራሳቸዉ በማንሳት ዉሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1723 እና 1724 መሠረት በጽሁፍ መደረግ ነበረበት፤ ይህ የጽሁፍ ማስረጃም አልቀረበም በማለት ዉሳኔ ሰጥተዋል፡፡ ይህ ዉሳኔ በግራ ቀኙ ወገኖች የቀረበዉን ክርክር መሠረት ያላደረገ እና ከስር ፍ/ቤት ጀምሮ ከተደረገዉ የክርክር ጭብጥ የወጣ እና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 328(2) እና 182(2) ድንጋጌዎችን ያላገናዘበ ነዉ፡፡ እንዲሁም የስር ፍ/ቤቶች በአመልካች የተነሳዉን የይርጋ ክርክር እልባት ሳይሰጡ ማለፋቸዉ ተገቢ አይደለም፡፡ በመሆኑም የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶቹ ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተሽሮ የወረዳዉ ፍ/ቤት ዉሰኔ እንዲጸና የሚጠይቅ ነዉ፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለክርክር መነሻ የሆነዉ ቤት የአመልካች አባት በ1970 ዓ.ም በተደረገ በልዋጭ የያዙት መሆኑን በምስክሮች መረጋገጡ እንዲሁም የለዉጥ ስምምነት ሲደረግ የተያዘዉ ቃለ-ጉባኤ ማስረጃ በ1983 ዓ.ም በመንግስት ለዉጥ ምክንያት የተቃጠለ መሆኑን ፍ/ቤቱ ባደረገዉ ማጣራት ሊያረጋግጥ መቻሉን ጠቅሶ ለአመልካች ካርታ ሊሰጣቸዉ ይገባል በሚል የወረዳዉ ፍ/ቤት የወሰነዉን በመሻር አመልካች ክርክር ያስነሳዉ ቤት በለዉጥ ስለመያዛቸዉ በሕግ አግባብ በጽሁፍ የተደረገ የለዉጥ ዉል ሰነድ በማቅረብ ባላስረዱበት ሁኔታ በተወረሰ ቤት ላይ ካርታ ሊሰጣቸዉ አይገባም በሚል ከክልሉ ዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ባሉት የመወሰኑን አግባብነት ከአዋጅ ቁጥር 47/67 አንቀጽ 16 አተገባበር እንዲሁም በዚሁ አዋጅ መሠረት በማድረግ በልዋጭ የሚያዙ ቤቶች አስመልክቶ በሰ/መ/ቁ 161565፣ 134963፣ 151748 እና በሌሎች መዛግብት ከተሰጠዉ ገዥ ትርጉም አንጻር ተጠሪዎች የሚያቀርበዉ ክርክር ተሰምቶ እንዲወሰን ሲባል ጉዳዩ በሰበር ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

ተጠሪዎች ለሰበር አቤቱታዉ ሚያዚያ 17 ቀን 2016 ዓ.ም የተዘጋጀ 3 ገጽ መልስ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱ በአጭሩ፡- ተጠሪዎች ለክርክር ምክንያት የሆነዉን ቤት ልዋጭ ከአመልካች አባት ጋር ያደረጉት ዉል የለም፡፡ ከአመልካች አባት ጋር የተደረገ የልዋጭ ሰነድ ወይም ቃለ-ጉባኤ አልቀረበም፡፡ የአመልካች ምስክሮችም በልዋጭ ዉል የተገኘ ነዉ ስለተባለዉ ቤት የሚያዉቁት ነገር እንደሌለ ገልጸዋል፡፡ አመልካች አባታቸዉ በሕይወት እያሉ ያልተጎናጸፉትን መብት ሊያገኙ አይችሉም፡፡ የአመልካች አባት በቁኒ ከተማ በነበራቸዉ ቤት ላይ አመልካች ያላቸዉን መብት ይጠይቁ እንጂ በአዋጅ መወረሱ በተረጋገጠዉ ቤት አመልካች ካርታ ወይም የይዞታ ማረጋገጫ ሊሰጣቸዉ አይችልም፡፡

በክልሉ አዋጅ ቁጥር 231/2013 አንቀጽ 2(12 እና 13) ስር ስለአደራ ቤት እና ስለተወረሰ ቤት በትክክል ትርጉም መሠረት የአመልካች አባት በአደራ የሰጠዉን ቤት በተመለከተ በአዋጁ አንቀጽ 47(2) ስር "የአደራ ቤት የሰጠ ሰዉ ያንኑ የሰጠዉን ቤት ይመለስልኝ በማለት የመጠየቅ መብት እንዳለዉ እና በንዑስ ቁጥር 3 ስር የራሱን ቤት አደራ የሰጠ ሰዉ በኪራይ በዉስጡ የሚኖርበትን ቤት በልዋጭ ወደ ራሱ ስም መቀየር እንደማይችል በግልጽ የተደነገገ በመሆኑ የአመልካች ጥያቄ ዉድቅ መደረጉ ተገቢ ነዉ፡፡

የማይንቀሳቀስ ንብረት ለሌላ ወገን ሊተላለፍ የሚችለዉ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1678፣ 1723 እና 1725 መሠረት የተቀመጡ መስፈርቶች ተሟልቶ ሲገኙ ብቻ መሆኑ ተደንግጓል፡፡ እንዲሁም በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2003፣ 2005 እና 2006 መሰረት አንድ በጽሁፍ ሰነድ ዉስጥ ያለ ፍሬ ነገር ሊስተባበል የሚችለዉ ቃለመሀላ በማስፈጸም እንጂ በሰዉ ምስክር ማስተባበል እንደማይቻል ተደንግጓል፡፡ የአመልካች ምስክሮች የአመልካች አባት ክርክር ያስነሳዉን ቤት በልዋጭ ስለማግኘቱም ሆነ ስለቤቱ እንደማያዉቁ የገለጹ በመሆናቸዉ የአመልካች ክርክር የሕግም ሆነ የፍሬ ነገር ድጋፍ የሌለዉ በመሆኑ ዉድቅ ተደርጎ በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተሰጥቶ በየደረጃዉ

ባሉት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ችሎቶች በተሰጠ ዉሳኔ የጸናዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አልተፈጸመበትም ተብሎ እንዲወሰን በመጠየቅ ተከራክረዋል፡፡

አመልካች ግንቦት 09 ቀን 2016 ዓ.ም የተዘጋጀ 3 ገጽ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸዉን በሚያጠናክር መልኩ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን እኛም አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡ የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር መርምረን እንደተረዳነዉ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሻዉ ጭብጥ፡- ለክርክር መነሻ የሆነዉ ቤት የአመልካች አባት በ1970 ዓ.ም በልዋጭ የያዙት መሆኑን በምስክሮች መረጋገጡ እንዲሁም የለዉጥ ስምምነት ሲደረግ የተያዘዉ ቃለ-ጉባኤ ማስረጃ በ1983 ዓ.ም በመንግስት ለዉጥ ምክንያት የተቃጠለ መሆኑን ፍ/ቤቱ ባደረገዉ ማጣራት ሊያረጋግጥ መቻሉን ጠቅሶ ለአመልካች ካርታ ሊሰጣቸዉ ይገባል በሚል የወረዳዉ ፍ/ቤት የወሰነዉን በመሻር አመልካች ክርክር ያስነሳዉ ቤት በለዉጥ ስለመያዛቸዉ በሕግ አግባብ በጽሁፍ የተደረገ የለዉጥ ዉል ሰነድ በማቅረብ ባላስረዱበት ሁኔታ በተወረሰ ቤት ላይ ካርታ ሊሰጣቸዉ አይገባም በሚል ከክልሉ ዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መወሰኑ ከአዋጅ ቁጥር 47/67 አንቀጽ 16 አተገባበር አንጻር ተገቢ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉን ነዉ፡፡

ክርክር ያስነሳዉ ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት ከሌሎች ግለሰቦች በመንግስት የተወረሰ መሆኑ፤ የአመልካች አባት በቁኒ ከተማ ቀበሌ 01 ዉስጥ የሚገኘዉን የግል ቤታቸዉን ለመንግስት በመስጠት በምትኩ ክርክር ባስነሳዉ ቤት ለረጅም ጊዜ ሲገለገሉበት መቆየታቸዉ አከራካሪ አይደለም፡፡ ግራ ቀኙን ያከራከረዉ ክርክር ያስነሳዉን ቤት የአመልካች አባት በልዋጭ አግኝተዉ የቤቱ ባለቤት በመሆናቸዉ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ሊሰጣሰጣቸዉ እንደሚገባ አመልካች የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪዎች በበኩላቸዉ ክርክር ያስነሳዉ ቤት በአዋጅ የተወረሰና በልዋጭ ለአመልካች አባት የተላለፈ ባለመሆኑ አመልካች የአባታቸዉ የሆነዉን በቁኒ ከተማ 01 ዉስጥ የሚገኘዉን የግል ቤታቸዉን ከሚጠይቁ በቀር በተወረሰ የመንግስት ቤት ላይ ካርታ ሊሰጣቸዉ አይገባም በሚል እየተከራከሩ ይገኛሉ፡፡ የወረዳዉ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃዎች መርምሮ ምንም እንኳ ልዋጭ የተደረገበት የዉል ሰነድ ባይቀርብለትም በ1970 ዓ.ም የአመልካች አባት ቤቱን የያዙበትን አግባብ የተመለከቱ ሰነዶች በ1983 ዓ.ም በመንግስት ለዉጥ ጊዜ መቃጠላቸዉን በማረጋገጥ፤ ከሌሎች ሰነዶችና ከምስክሮች ቃል የአመልካች አባት ቤቱን በልዋጭ ማግኘታቸዉን ማረጋገጡን እና በአዋጅ የተወረሰን ቤት በልዋጭ ወይም ግምት በመክፈል ማስተላለፍን አዋጅ ቁጥር 47/67 እንደማይከለክል እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል አዋጅ ቁጥረ 231/2013 አንቀጽ 49/2 መሠረት በአደራ ከተያዘና በኪራይ ከተያዘዉ ቤት መካከል በመምረጥ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ መዉሰድን

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የግሉን በአደራ ለሰጠዉ ሰዉ የሚፈቅድ በመሆኑ ለአመልካች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንዲሰጣቸዉ ሲል ወስነዋል፡፡

በሌላ በኩል የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ሆነ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በበኩላቸዉ የወረዳዉን ፍ/ቤት ዉሳኔ የሻሩት የማይንቀሳቀስ ንብረት ለማስተላለፍ የሚደረግ ዉል በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1723 እና 1725 መሠረተ በጽሁፍ ተደርጎ መመዝገብ ያለበት ቢሆንም የልዋጭ ዉል ሰነድ አለመቅረቡን፤ በምስክሮችና ለድጋፍ በተጻፉ ሰነዶች ልዋጭ መኖሩን ማረጋገጥ እንደማይቻል፤ አመልካች አባታቸዉ በልዋጭ አገኙ እንጂ በአደራ አገኙ የሚል የዳኝነት ጥያቄ የሌላቸዉ በመሆኑ ባልጠየቁት ዳኝነት አዋጅ ቁጥር 231/2013 አንቀጽ 49(2) ተፈጻሚ እንደማይሆንላቸዉ በመግለጽ ክርክር ባስነሳዉና በመንግስት በተወረሰ ቤት ላይ ለአመልካች ካርታ ሊሰጣቸዉ አይገባም በሚል ነዉ፡፡ አመልካች አጥብቀዉ የሚከራከሩት የልዋጭ ስምምነቱን በተመለከተ በ1983 ዓ.ም በተደረገ የመንግስት ለዉጥ ወቅት ዋናዉ መዝገብ የተቃጠለ በመሆኑ ከቤቱ ጋር የተያያዘ ሰነድ ሊገኝ አለመቻሉ በተረጋገጠበት በምስክርና በሌሎች ማስረጃዎች ማስረዳት አይቻልም መባሉ ስህተት ነዉ በሚል ሲሆን ተጠሪዎች በበኩላቸዉ ክርክር ያስነሳዉ ቤት ከሌሎች ግለሰቦች የተወረሰ መሆኑ እስከተረጋገጠና የልዋጭ ዉል እስካልቀረበ ድረስ በተወረሰ የመንግስት ቤት ላይ ለአመልካች ካርታ ሊሰጣቸዉ አይገባም በሚል ነዉ፡፡

በመሠረቱ የማይንቀሳቀስ ንብረት በሽያጭ ወይም በለዉጥ የማስተላለፍ ዉል በጽሁፍ ሊደረግ የሚገባዉ መሆኑን ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 1723(1) እና 2877 ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻል ሲሆን የማስተላለፍ ዉሉ መኖሩን ማስረዳት የሚቻለዉ በመርህ ደረጃ የዉሉን ሰነድ በማቅረብ መሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2008(1) ስር ተመልክቷል፡፡ ሆኖም በልዩ ሁኔታ የዉል ሰነዱ ከተቀደደ፣ ከተሰረቀ ወይም የጠፋ መሆኑ ሲረጋገጥ በምስክሮች ወይም በህሊና ግምት ማስረዳት እንደሚቻል ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 2003 ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻል ነዉ፡፡ ይህን አስመልክቶ የፌዴራል ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 69203 እና በሌሎች መዛግብት ገዥ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

በሌላ በኩል በአዋጅ ቁጥር 47/67 ተወርሶ የመንግስት የሆነ ቤት በማናቸዉም መንገድ ለግለሰብ ሊተላለፍ አይችልም ተብሎ ሊደመደም የሚያስችል ክልከላ ካለመኖሩም በላይ የኦሮሚያ ክልል አዋጅ ቁጥር 231/2013 በተለይ በአንቀጽ 47 እና 49 ስር የመንግስት ቤት በልዋጭ፣ በአደራ ወይም በኪራይ ሲያዝ ለያዡ ወገን የማይዘዋወርበት ወይም ተዘዋዉሩ ካርታ የሚሰጥበት አግባብ መኖሩ የተደነገገ በመሆኑ በአዋጅ ተወርሶ የመንግስት ሆኖ የነበረ ቤት በምንም መልኩ ወደ ግለሰብ ሊተላለፍ አይችልም ተብሎ ሊደመደም የሚችል አለመሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረዉ የአመልካች አባት በቁኒ ከተማ 01 ቀበሌ የነበራቸዉን የግል ቤታቸዉን ለአስተዳደሩ በማስረከብ በምትኩ ክርክር ባስነሳዉና ከግለሰቦች በአዋጅ ቁጥር 47/67 በተወረሰ

ቤት ሲገለገሉ መቆየታቸዉ አከራካሪ አይደለም፡፡ አከራካሪዉ ነጥብ የአመልካች አባት በምን አግባብ ወይም ስምምነት ነዉ ክርክር ያስነሳዉን ቤት ይዘዉ ሲገለገሉበት የቆዩት የሚለዉ ነዉ፡፡ የወረዳዉ ፍ/ቤት ምንም እንኳ ተጠሪዎች እንደሚሉት የለዉጥ ዉል ስምምነት ባይቀርብለትም የአመልካች አባት ቤቱን የያዙት በግለሰቦች መካከል በሚደረግ ባለቤትነትን ለማስተላለፍ በሚደረግ ዉል ዓይነት ሳይሆን አዋጅ ቁጥር 47/67 በሚፈቅደዉ ስርዓት መሆኑን ግምት ዉስጥ በማስገባትና በምን አግባብ እንደተላለፈ የሚገልጹ ሰነዶች የያዘ መዝገብ በ1983 ዓ.ም በተደረገዉ የመንግስት ለዉጥ ወቅት በመቃጠሉ ምክንያት ሊገኝ አለመቻሉን በማረጋገጥ በምስክሮች ቃል እና በሌሎች የሰነድ ማስረጃዎች ላይ ተመስቶ የአመልካች አባት ክርክር ያስነሳዉን ቤት በልዋጭ የገኙት መሆኑን አረጋግጦ በአዋጅ ቁጥር 231/2013 አንቀጽ 49(2) መሠረት አመልካች ካርታ እንዲሰጣቸዉ ወስኗል፡፡

በሌላ በኩል የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የክልሉ ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአመልካች አባት ቤቱን አገኙ የተባለበትን ልዩ ሁኔታ እና ስለሁኔታዉ የሚያስረዱ ሰነዶች ወይም መዝገብ በ1983 ዓ.ም በነበረዉ የመንግስት ለዉጥ ወቅት የተቃጠሉ መሆናቸዉን የተረጋገጠበትን ወደ ጎን በመተዉ እና በግራ ቀኙ በኩል የቀረበዉን ማስረጃ ሳይመዝኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1723 መሠረት አመልካች የለዉጥ ዉል መኖሩን የዉል ሰነድ በማቅረብ አላስረዱም ተብሎ በደፈናዉ የወረዳዉ ፍ/ቤት መሻሩ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 2003 ድንጋጌን፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 69208 እና በሌሎች መዛግብት የሰጠዉን አስገዳጅ ትርጉም ያለገናዘበና ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ ነዉ፡፡

ሌላዉ ምንም እንኳ አመልካች ክርክር ባስነሳዉ ቤት ላይ የይዞታ ወይም የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ እንዲሰጣቸዉ ዳኝነት የጠየቁት አባታቸዉ ቤቱን በልዋጭ ያገኙት መሆኑን በመግለጽ ቢሆንም በግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ ቤቱን የያዙት አግባብ የተረጋገጠዉ በልዋጭ ወይም በአደራ ወይም በኪራይ ወይም በሌላ አግባብም ቢሆን ዋናዉ የዳኝነት ጥያቄያቸዉ ካርታ ይሰጠኝ የሚል እንደመሆኑ መጠን የወረዳዉ ፍ/ቤት በተጨማሪ ምክንያትነት በአዋጅ ቁጥር 231/2013 አንቀጽ 49(2) መሠረት ለአመልካች ካርታዉ እንዲሰጥ የሰጠዉን ዉሳኔ አመልካች በልዋጭ ባገኙት ቤት ላይ እንጂ በአደራ ባገኙት ቤት ላይ ካርታ እንዲሰጣቸዉ አልጠየቁም በማለት ባልተጠየቀ ዳኝነት የተሰጠ ዉሳኔ እንደሆነ በመቁጠር የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ለዉሳኔዉ በምክንያትነት መጠቀሙ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 182 እና አመልካችን የዳኝነት ጥያቄ አድማስ ያላገናዘበ በሆኑ ተገቢ አይደለም፡፡

ከላይ ከተገለጹት ምክንያቶች መነሻነት ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ማስረጃን መዝኖ ፍሬ ነገርን ለማረጋገጥ ስልጣን ያልተሰጠዉ በመሆኑና ተጠሪዎች በወረዳዉ ፍ/ቤት ዉሳኔ ላይ ቅር ተሰኝተዉ ለዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ካቀረቡት ይግባኝ አንጻር የግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃዎች ተመርምረዉና ተመዝነዉ የአመልካች አባት ክርክር ያስነሳዉን ቤት ይዘዉ ሲገለገሉበት የነበሩት በልዋጭ ወይም በአደራ ወይም በሌላ በምን

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አግባብ መሆኑን በማረጋገጥ ከአዋጅ ቁጥር 47/67 እና ከክልሉ አዋጅ ቁጥር 231/2013 ድንጋጌዎች አንጻር የወረዳዉ ፍ/ቤት ለአመልካች ካርታ ወይም የይዞታ ማረጋገጫ እንዲሰጣቸዉ መወሰኑ ተገቢ ነዉ ወይስ አይደለም? በሚሉት ነጥቦች ላይ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተገቢዉን እንዲወስን ጉዳዩ ሊመለስት የሚገባዉ ነዉ፡፡

ሲጠቃለል የምዕራብ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም ሆነ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የአመልካች አባት ክርክር ያስነሳዉን ቤት ይዘዉ ለረጅም ጊዜ ሲገለገሉበት የቆዩበትን አግባብ ለማስረዳት ሊቀርብ የሚችለዉ ዋና የሰነድ ማስረጃና መዝገብ በ1983 ዓ.ም በተደረገዉ የመንግስት ለዉጥ ወቅት የተቃጠለ መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ እና የአመለካችን የዳኝነት ጥያቄ አድማስ ባላገናዘበ መልኩ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1723 መሰረት የቤት ልዋጭ ዉል መኖሩን የሚያረጋገጥ የዉል ሰነድ አልቀረበም በሚል የወረዳዉን ፍ/ቤት ዉሳኔ በመሻር የሰጡት ዉሳኔ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 2003 እና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 182 ድንጋጌዎችን እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 69208 እና በሌሎች መዛግብት የሰጠዉን ገዥ ትርጉም ያላገናዘበ፤ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሸ) እና 10(1/ሐ) አንጻር መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በምዕራብ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 62518 ግንቦት 25 ቀን 2014 ዓ.ም ተሰጥቶ፤ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 400772 ግነቦት 11 ቀን 2015 ዓ.ም በተሰጠ ዉሳኔ እና በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 424319 ሰኔ 08 ቀን 2015 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ የጸናዉ ዉሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የምዕራብ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የዘጋዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ ከላይ በፍርድ ሀተታዉ ላይ በተገለጸዉ አግባብ ተጠሪዎች ካቀረቡት ይግባኝ፤ በግራ ቀኙ መካከል ከተደረገዉ ክርክርና ከቀረበዉ ማስረጃ አንጻር ክርክር ያስነሳዉን ቤትና ይዞታ የአመልካች አባት ይዘዉ ለረጅም ጊዜ ሲገለገሉ የቆዩበትን አግባብ በማረጋገጥ እንዲሁም የወረዳዉ ፍ/ቤት ከአዋጅ ቁጥር 47/67 እና ከክልሉ አዋጅ ቁጥር 231/2013 ድንጋጌዎች አንጻር ለአመልካች ካርታ ወይም የይዞታ ማረጋገጫ እንዲሰጣቸዉ የሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢ መሆን አለመሆኑን አስመልክቶ ዉሳኔ ይሰጥበት ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343(1) እና በሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(2) መሰረት ጉዳዩን መልሰንለታል፡፡ ይጻፍ፡፡
3. በዚህ መዝገብ ሕዳር 27 ቀን 2016 ዓ.ም የተሰጠዉ የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ/ጋ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ. 250866
ቀን ፡- ጥቅምት 07 ቀን 2017 ዓ/ም

ዳኞች- እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች፡- ወ/ሮ ሰላማዊት ተሾመ ጠበቃ አብደላ ዓሊ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ብርሃን አርጋው ቀረቡ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው በመሆኑ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**<u>ፍርድ</u>**

ጉዳዩ ባልና ሚስት የንብረት ክርክር የሚመለከት ሲሆን አመልካች የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት በተደረገ ክርክር አመልካች ከሳሽ፤ ተጠሪ ተከሳሽ እና በዚህ ፍርድ ቤት ተከራካሪ ያልሆኑት አቶ ዮሃንስ አርጋው ደግሞ ጣልቃ ገብ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- ከተጠሪ ጋር ጋብቻ ሳንፈፅም ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ እንደባልና ሚስት አብረን ስንኖር የተለያዩ ንብረቶችን አፍርተናል ከነዚህም ውስጥ አሁን በዚህ ችሎት አከራካሪ ሆኖ የቀረበው  በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለከተማ ወረዳ 06 ብሎክ 04 የቤት ቁጥር

<u>ማስታወሻ</u>፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

BOO4/15 የሆነው የኮንዶሚየም ቤት የጋራ ሀብታችን ስለሆኑ ድርሻዬ ያካፍለኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ተጠሪ በሰጡት መልስ ኮንዶሚኒየም ቤት ወንድሜ ማርቆስ አርጋው ከዚህ አለም በሞት ሲለይ ከሌላ ወንድሜ ጋር በውርስ ያገኘነው በልማት የፈረሰ የቀበሌ ቤት ምትክ ቤት ነው በመሆኑም ከአመልካች ጋር በጋራ የተፈራ አይደለም ንብረቱ ላይም አመልካች አስተዋጽኦ አላደረጉም ሊካፈሉ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የሥር ጣልቃ ገብ አቶ ዮሐንስ አርጋው በበኩላቸው ጣልቃ በመግባት አመልካች በክሳቸው ላይ የጠቀሱት ኮንዶሚኒየም ወንድማችን ማርቆስ አርጋው ከዚህ አለም በሞት ሲለይ በውርስ ለተጠሪ እና ለጣልቃ ገብ የተላለፈ እና ካርታውም በእነ ብርሃን አርጋው እና ዮሃንስ አርጋው ስም የተመዘገበ ነው፣ አብረን ለመኖር ቤቱ ስለማይበቃን ከአመልካች ጋር እንዲኖሩበት ፈቅጄላቸው ድርሻ እንዲሰጠኝ እና ስመ ሃብቱ እንዲዞር ብንስማማም እስካሁን ስላልከፈሉኝ ስመ ሃብቱ ሳይዞር ቀርቷል በመሆኑም ቤቱ የአመልካች እና የተጠሪ የጋራ ሃብት አይደለም ተብሎ እንዲወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ጣልቃ ገብ ባቀረቡት አቤቱታ ላይ በሰጡት መልስ  ጣልቃ ገብ በስምምነታቸው መሰረት 27000 ( ሃያ ሰባት ሺ ) ተከፍሏቸው ስመ ሃብቱም ዞሯል፣ የሽያጭ እና ግብይት ውሉም የተፈጸመው የውርስ ድርሻው ቅድሚያ ተከፍሎ ነው በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክሮች እና የቀረቡ ማስረጃዎችን አግባብነት ካለው ህግ ጋር በመመርመር የኮንዶሚኒየም ቤት ካርታ የሚያሳየው ቤቱ የተጠሪ እና ጣልቃ ገብ መሆኑን ነው፣ እንዲሁም አመልካች ቤቱ ለተጠሪ የተላለፈው በውርስ መሆኑን አምነው ነገር ግን እዳው የተከፈለው ከጋራ ንብረት ላይ ነው ቢሉም አመልካች የተከፈለውን የቤት እዳ ተጠሪ ያካፍለኝ የሚል ክርክር አላነሱም፡፡ ኮንዶሚኒየም ቤት ለተጠሪ በውርስ የተላለፈ በመሆኑ ንብረቱ የተጠሪ የግል ንብረት ነው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ፍርድ ቤቱ ለዚህ ሰበር ምክንያት ባልሆኑ ሌሎች ጉዳዮች ላይም ተገቢነው ያለውን ውሳኔ አስተላልፏል፡፡ አመልካች ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ይግባኙን በመመርመር ቅሬታ የቀረበበት ውሳኔ ስህተት ያለበት ሆኖ ስላልተገኘ ይግባኙን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

አመልካች ሐምሌ 14 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይህን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ሲሆን ይዘቱም፦ ክርክር የተነሳበት ቤት የካርታው የፊት ለፊት ገጽ ላይ ካርታው የተሰጠው የካቲት 01 ቀን 2002 ዓ.ም መሆኑንና በተጠሪ እና በአቶ ዮሐንስ አርጋው ስም ተመዝግቦ የነበረ መሆኑን የሚያሳይ ቢሆንም ካርታው ጀርባ ላይ የቤቱ ባለሀብትነት አመልካችና ተጠሪ አብረው በነበሩበት ወደ ተጠሪ ባለሀብትነት የተላለፈ መሆኑን የሚያስረዳ ሆኖ እያለ የሥር ፍርድ ቤት ካርታው የሚያሳየው ቤቱ የአቶ ተጠሪ እና የሥር ጣልቃ ገብ መሆኑን ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የሥር ጣልቃ ገብ ድርሻቸውን የለቀቁ ሲሆን ድርሻ ክፍያ ገንዘቡ የተከፈለው ከተጠሪ ጋር ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት ከጀመረን በኋላ በመሆኑ ቤቱ የጋራ ሀብት ሆኗል ንብረቱ ተጠሪ የግል ሀብት ነው መባሉ የቤተሰብ ሕጉን ያልተከተለ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የሰበር ሰሚው ችሎትም የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ በስር ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር አከራከሪው የኮንዶሚንየም ቤት ከስር ጣልቃገብ ጋር በተደረገ ስምምነት መሠረት ብር 27,000 ተከፍሏቸዋል፣ ስመ ሐብቱም ዞሯል፣ ውሉ የተፈጸመውም የውርስ ድርሻው ቅድሚያ ተከፍሎ ነው በማለት በተከራከሩበት ሁኔታ ይህ ክርክራቸው በጭብጥነት ተይዞ እና በማስረጃ ተረጋግጦ ሊወሰን ሲገባው ይህ ሳይደረግ የኮንዶሚንየም ቤቱ በውርስ የተላለፈ በመሆኑ የተጠሪ የግል ሀብት ነው በሚል የመወሰኑ አግባብነት ሊመረመር የሚገባው በመሆኑ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ታዟል ፡፡

ተጠሪ ሚያዝያ 17 ቀን 2016 ዓ.ም የሰጡት መልስ ይዘት፡- አስቀድሞ በኪራይ የተያዘ የመንግስት ቤት የነበረ ቢሆንም ቦታው ለልማት ሲፈለግ በምትክነት የተገኘ የኮንዶሚኒየም ቤት ነው፣ በቤቱ ውስጥ አብረን አብረን ለመኖር ከሥር ጣልቃ ገብ ባለመስማማታችን ድርሻ ለመልቀቅ ሥምምነት ያደረግን ሲሆን ከሥምምነት ገንዘቡ ብር 7,000.00 ለጣልቃ ገብ የተከፈለ ስለመሆኑ እና እንደገና በተደረገ ሥምምነት ብር 27,000.00 ለመክፈል ግዴታ የገቡ ስለመሆኑ፣ በዚህ ሥምምነት መሠረት የቤቱ ሥመ-ሀብት ወደተጠሪ በመዛወሩ ምክንያት የጣልቃ-ገብ ጥያቄ በሥር ፍርድ ቤት ውድቅ መደረጉንና ገንዘቡን ግን እስካሁን ለጣልቃ ገብ ያልተከፈለ ስለመሆኑ በመጥቀስ ንበረቱ የተጠሪ የግል ሀብት ነው ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ሊጸና ይገባል ብለዋል፡፡ አመልካች በሰጡት የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ህጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

እንደመረመርነው ጉዳዩ ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት በነበረ ግንኙነት መቋረጥ ጋር በተያያዘ የቀረበ የንብረት ክፍፍል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ዋናው የክርክር ጭብጥ ክርክር ያስነሳው በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለከተማ ወረዳ 06 ብሎክ 004 የቤት ቁጥር B004/15 የሆነ ኮንዶሚኒየም ቤት ግራቀኙ ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት የነበራቸው ግንኙነት ከመጀመሩ በፊት አስቀድመው ተጠሪ ያፈሩት የግል ንብረት ነው ወይስ ከአመልካች ጋር ግንኙነቱ ውስጥ እያሉ የተፈራ የጋራ ንብረት ነው የሚለው ነው፡፡ ክርክሩን በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሰረት መምራት እና መቆጣጠር የፍርድ ቤቱ ኃላፊነት ሲሆን በተገቢው ሁኔታ ካልተመራ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ዓላማዎች የሆኑትን እንደ አንጻራዊ እውነትን የመፈለግ፣ ሥነ-ሥርዓታዊ ፍትህ፣ ክርክርን ውጤታማ፣ ወጭና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ መምራት የመሳሰሉትን ማሳካት ስለማይቻል የተከራካሪዎችን መብት ይነካል፡፡ ክርክር የሚወሰነው በተጠየቀው ዳኝነት

አግባብ እንደሆነ የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 182(2) ላይ ተመልክቷል፡፡ ፍርድ ቤቱም ከቀረበው ዳኝነት አኳያ ከግራቀኙ ክርክር በመነሳት በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 246 እና ተከታዮቹ መሠረት በተነሱት ጉዳዮች ጭብጥ መስርቶ ውሳኔ የመስጠት ኃላፊነት አለበት፡፡ በክርክር አመራር ሥርዓት ሂደቱ የግራቀኙ ንብረት ክፍፍል እና የሀብት ማጣራት ስራ ሲከናወን በቤተሰብ ሕጉ ንብረት ስለሚጣራበት ሁኔታ የተዘረጋውን ሥርዓት ግምት ውስጥ ማስገባት ይገባል፡፡

ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት የነበረ ግንኙነት ከሦስት ዓመት በላይ ከቆየ በፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 102/1/ መሠረት በግንኙነቱ ውስጥ ያፈሯቸውን ንብረቶች የጋራ ሀብታቸው ይሆናሉ፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራቀኙ ግንኙነት ከሦስት ዓመት በላይ የቆየ መሆኑን በማረጋገጡ የንብረት ክፍፍል ክርክሩን መመልከቱን ተረድተናል፡፡ ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት የነበረ ግንኙነት ሲቋረጥ ስለሀብት ማጣራት በፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 85 እና ተከታይ ድንጋጌዎች የተመለከቱ ተፈጻሚነት ያላቸው ስለመሆኑ ከአንቀጽ 103 ይዘት የምንገነዘበው ነው፡፡ ንብረቱ የተፈራው ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት በነበረው ግንኙነት ውስጥ ወይስ ከግንኙነቱ በፊት የሚለው የፍሬ ነገር ጭብጥ ነው፤ በክርክር ሂደት ፍሬ ነገሮችን ማረጋገጥ የሚቻልባቸው ዘዴዎች ማስረጃ፣ በፍርድ ቤት በሚሠጥ የእምነት ቃል፣ ፍርድ ቤት በራሱ ግንዛቤ ሊወስድባቸው የሚችሉ ጉዳዮች፣ የሕግ ግምት እና የመሓላ ቃል ናቸው፡፡ በፍትሐ ብሔር ክርክር የምንከተለው የማስረዳት ደረጃ ከሁለቱ ወገን የተሻለ ያስረዳው ማን ነው (preponderance of evidence) የሚለውን በመመርመር ነው፤የማስረጃ ተገቢነት፣ የማስረጃው ተቀባይነትን ደንቦችን መከተል እና ለማስረጃው የሚሰጠውን ክብደት በመለየት የመወሰን ኃላፊነት ማስረጃ ለመስማትና ለመመዘን ኃላፊነት ያለባቸው ፍርድ ቤቶች ዋና ተግባር ነው፡፡

ማስረጃ ለመመዘን ሥልጣን የተሠጠው ፍርድ ቤት ማስረጃ ሲቀበል የተከራካሪዎችን እኩል የመደመጥ መብት ካላከበረ፣ የማስረዳት ሸክም (burden of production) የማን ነው የሚለውን ካልለየ፣ የማስረጃ ተቀባይነትና ተገቢነት ላይ መከተል የሚገባውን ሥርዓት ካልተከተለ፣ በምዘና ጊዜ የሁሉንም ተከራካሪዎች ማስረጃ አብሮ ካልመዘነ፣ ከማስረዳት ደረጃ (standard of proof) አንጻር በሚጠይቀው ደረጃ ልክ መረጋገጡን ካላሳየ እና በመሠረታዊ ሕግ ሆነ በሥነ-ሥርዓት ሕግ ያሉትን የማስረጃ ሕጎችና መርሆች ካላከበረ ጉዳዩ የማስረጃ ምዘና ሳይሆን የሕግ አተረጓጎም ስህተትና ፍርድ ቤት ያለበትን ኃላፊነት አለመወጣት ስለሚሆን የሰበር ሰሚ ችሎቱ የሚመለከተው ጉዳይ ስለመሆኑ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 172206 እና ሌሎች በርካታ መዝገቦች ላይ አስገዳጅ ትርጉም የተሰጠበት ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን ከሰማ በኋላ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለከተማ ወረዳ 06 ብሎክ 004 የቤት ቁጥር B004/15 የሆነ ኮንዶሚኒየም ቤት የተመዘገበው በተጠሪና በስር ፍርድ ቤት ጣልቃ ገብተው የተከራከሩት የተጠሪ ወንድም አቶ ዮሐንስ አርጋው ስም ስለመሆኑ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በውሳኔው ላይ ገልጿል፡፡ በሌላ በኩል ጣልቃ ገብ በሥር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክርክር ቤቱ ያላቸውን ድርሻ ለተጠሪ ለማስተላለፍ ሥምምነት ማድረጋቸውን ነገር ግን እስካሁን ክፍያ እንዳልተፈጸመላቸው ጠቅሰው የተከራከሩ ሲሆን አመልካች ለጣልቃ ገብ ክርክር በሰጡት መልስ በድርሻ መልቀቅ ሥምምነቱ መሠረት ብር 27,000.00 ተከፍሏቸው ሥመ-ሀብቱም የዞረ ስለመሆኑ ክርክር አቅርበዋል፡፡ ተጠሪም ለዚህ ችሎት ባቀረቡት መልስ ላይ ከሥር ጣልቃ ገብ ወንድማቸው ጋር ከሥምምነት ገንዘቡ ብር 7,000.00 ለጣልቃ ገብ የተከፈለ ስለመሆኑ እና እንደገና በተደረገ ሥምምነት ብር 27,000.00 ለመክፈል ግዴታ የገቡ ስለመሆኑ፣ በዚህ ሥምምነት መሠረት የቤቱ ሥመ-ሀብት ወደተጠሪ በመዛወሩ ምክንያት የጣልቃ-ገብ ጥያቄ በሥር ፍርድ ቤት ውድቅ መደረጉንና ገንዘቡን ግን እስካሁን ለጣልቃ ገብ ያልተከፈለ ስለመሆኑ ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቶች በክርክር የተነሱ ፍሬ ነገሮች ላይ ጭብጥ በመመስረትና ፍሬ ነገሩን በማስረጃ አጣርተው የሕግ ውጤቱን የመወሰን ኃላፊነት እንዳለባቸው ከፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 246 እና ተከታይ ድንጋጌዎች አቀራረጽ የምንገነዘበው ነው፡፡ ክርክር ያስነሳው ኮንዶሚኒየም ቤት አስቀድሞ የተጠሪና የሥር ጣልቃ ገብ ወንድማቸው የነበረ ስለመሆኑ ከግራቀኙ ክርክር መረዳት ይቻላል፡፡ የሥር ጣልቃ ገብ አቶ ዮሐንስ አርጋው የድርሻ መልቀቅ ሥምምነት አድርገዋል፣ ሥምምነቱም ተፈጽሟል የሚል ክርክር የቀረበ በመሆኑ ይሕ ፍሬ ነገር በጭብጥነት ተይዞ ሊጣራ ይገባው ነበር፤ የድርሻ መልቀቅ ሥምምነቱ መቼ ተደረገ፣ የአመልካችና የተጠሪ ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት ውስጥ የተደረገ ሥምምነት ነው ወይስ አይደለም፣ በድርሻ መልቀቅ ሥምምነቱ መሠረት ብር 7,000.00 የተከፈለው መቼ ነው፣ በሥምምነቱ መሠረት ገንዘቡ በሙሉ ተከፍሏል ወይስ አልተከፈለም፣ የድርሻ መልቀቅ ሥምምነቱ የተደረገው አመልካች ከተጠሪ ጋር ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት ከጀመሩ በኋላ ከሆነ ሕጋዊ ውጤቱ ምንድን ነው፣ አመልካች በንብረቱ ላይ ያላቸው ድርሻ ምን ያሕል ነው የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ ክርክሩ ሊወሰን ሲገባ በዚህ አግባብ አለመከናወኑና ይግባኝ ሰሚ ችሎቱም ይሕንን ሳያርም ማለፉ መሠረታዊ የሆነ የክርክር አመራር ግድፈት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 303820 ሰኔ 14 ቀን 2015 ዓ/ም እና የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 176525 መጋቢት 06 ቀን 2015 ዓ/ም የሰጡት ውሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1)(ለ) መሰረት ተሻሽሏል፡፡

<u>ማስታወሻ፡</u>- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

2. በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለከተማ ወረዳ 06 ብሎክ 004 የቤት ቁጥር B004/15 የሆነ ኮንዶሚኒየም ቤት ላይ የተሰጠው ውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡ ቀሪው የውሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡

3. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በውሳኔ የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለከተማ ወረዳ 06 ብሎክ 004 የቤት ቁጥር B004/15 የሆነ ኮንዶሚኒየም ቤት አስመልክቶ የሥር ጣልቃ ገብ አቶ ዮሐንስ አርጋው የድርሻ መልቀቅ ሥምምነት አድርገዋል፣ ሥምምነቱም ተፈጽሟል የሚል ክርክር የቀረበ በመሆኑ ይሕ ፍሬ ነገር በጭብጥነት ተይዞ ሊጣራ ይገባው ነበር፤ የድርሻ መልቀቅ ሥምምነቱ መቼ ተደረገ፣ የአመልካችና የተጠሪ ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት ውስጥ የተደረገ ሥምምነት ነው ወይስ አይደለም፣ በድርሻ መልቀቅ ሥምምነቱ መሠረት ብር 7,000.00 የተከፈለው መቼ ነው፣ በሥምምነቱ መሠረት ገንዘቡ በሙሉ ተከፍሏል ወይስ አልተከፈለም፣ የድርሻ መልቀቅ ሥምምነቱ የተደረገው አመልካች ከተጠሪ ጋር ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት ከጀመሩ በኋላ ከሆነ ሕጋዊ ውጤቱ ምንድን ነው፣ አመልካች በንብረቱ ላይ ያላቸው ድርሻ ምን ያሕል ነው የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ ግራቀኙን በማከራከርና ማስረጃ በመስማት በሕግ መሠረት ውሳኔ እንዲሰጥበት በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(2) መሠረት ጉዳዩን መልሠናል፡፡

4. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በውሳኔው መሠረት እንዲፈጽም አዟናል፡፡ ይጻፍ
- አፈጻጸሙ ላይ የተሰጠው እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ/ጋ

<u>ማስታወሻ</u>፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መ/ቁ/250900
ጥቅምት 05 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች፡ ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

ሠናይት አድነው

ሀፊዝ አባጀማል

አመልካች፤አቶ ዘዉገ መዓዛ

ተጠሪዎች፤ 1.አቶ ኃይለገብርኤል ሽፈራዉ

2. ተማሪ ሰናይት ሽፈራው

3. የኢትዮጲያ መድን ድርጅት

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

**ፍርድ**

ጉዳዩ የጉዳት ካሳ ክርክርን የሚመለከት ሆኖ ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው የአብከመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 01-21402 ታህሳስ 22 ቀን 2014 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ እና የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.221959 ግንቦት 25 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ውሳኔ ላይ ተፈጽሟል ያሉትን መሠረታዊ የሕግ ስህተት በመጥቀስ በሰበር ታይቶ እንዲታረም የአሁን አመልካች ሐምሌ 13 ቀን 2015 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡

ጉዳዩ በተጀመረበት የአብከመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች 2ኛ ተከሳሽ 1ኛ ተጠሪ 1ኛ ተከሳሽ 2ኛ ተጠሪ ከሳሽ 3ኛ ተጠሪ ደግሞ 1ኛ ጣ/ገብ የነበሩ ሲሆን የ 2ኛ ተጠሪ ክስ ባጭሩ፤ ከሳሽ ንብረትነቱ የ1ኛ ተከሳሽ በሆነ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ.3-33889 ኦሮ በሆነ የህዝብ አይሱዙ የትራንስፖርት ክፍያ ከፍዬ ከአዲስ አበባ ወደ ደ/ብርሃን በመንዝ ላይ እያለን መኪናዉ የራሱን ቀኝ መስመር ወደ ተቃራኒ ግራ መስመር 2ሜ ከ33 ሴ.ሜ አልፎ በመግባት ከደ/ብርን ወደ አዲስ አበባ በመንዝ ላይ ከነበረ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 3-55830 ኢቲ ኒሳን መኪና ጋር በመጋጨቱ ምክንያት የእግር ስብራት አደጋ የደረሰባት በመሆኑ በወቅቱ 22አመቷ የነበረ እና ለመመረቅ አንድ ኮርስ የቀራት በመምህርነት ሙያ ለመሰማራት የነበረ ቢሆንም በአደጋዉ መክንያት ስላልተመረቀች በመምህርትነት ተቀጥራ ልታገበኝ የምትችለዉን ገቢ 100% ያጣች በመሆኑ በብሄራዊ ሰታቲክስ መረጃ መሰረት ለ41.5 የመኖር ዕድል የነበራት በመሆኑ 1ኛ ተከሳሽ የተቋረጠ ገቢ፤ የህክምና መድኃኒት መግዣ፤ የህክምና ማስረጃ ማስተርጎምያ፤ የትራንስፖርት ወጭ፤ የገንቢ ምግብ ወጭ፤ የ40 ቀን የአስታማሚ ምግብ ወጭ፤ ከሆስፒታል ዉጭ ለተመላላሽ ህክምና ቤት ኪራይና የሰራተኛ ወጭ፤ ለሰዉ ሰራሽ አካል መደገፍያ እና ለንጽህና መጠበቅያ ወጭ እና የሞራል ካሳ ጠቅላላ ብር 1,954,902.88 1ኛ ተከሳሽ እንዲከፍል እንዲወሰንልኝ የሚል ነዉ፡፡

1ኛ ተከሳሽ በሰጠዉ መልስ፤ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ወደ ክሱ እንዲገባ ከጠየቁ በኋላ አደጋዉ የደረሰዉ በ1ኛ ተከሳሽ ሳይሆን በ2ኛ ተከሳሽ መኪና በመሆኑ ልንጠየቅ አይገባም፤ ከሳሽ አደጋዉ በደረሰ ጊዜ ገቢ የሚያስገኝ ስራ ላይ አልነበረችም የተቋረጠም ገቢ የለም፤ የተጠየቀዉ ወጪም የተጋነነ ነዉ ልንጠየቅ አይገባም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

2ኛ ተከሳሽም በሰጠዉ መልስ ንብ ኢንሹራንስ ወደ ክርክሩ እንዲገባ ከጠየቀ በኋላ አደጋዉ የደረሰዉ በ2ኛ ተከሳሽ መኪና ሳይሆን በ1ኛ ተከሳሽ መኪና በመሆኑ ልንጠየቅ አይገባም፤ ከሳሽ በመምህርነት ልትቀጠር እንደምትችል የቀረበ ማስረጃ የለም እንዲሁም የቀረበዉ ወጪ የተጋነነ ነዉ በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

1ኛ ጣ/ገብ በሰጠዉ መልስ፤ አደጋዉ የደረሰዉ በእኔ ደንበኛ መኪና አይደለም በ1ኛ ተከሳሽ መኪና በመሆኑ የደንበኞችን መኪና ጥፋት ስለሌለበት ልንጠየቅ አይገባም፤ኃላፊነት አለባቹ ከተባልንም በመድን ዉሉ መሰረት ኃላፊነታችን ብር 40,000 ብቻ ነዉ፡፡ የወደፊት ጉዳት ካሳ የሚጠየቀዉ ሊደርስ በሚችል በተረጋገጠ ጉዳት ብቻ እንጂ መምህርት ልትሆን ትችል ነበር በሚል ግምት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ሊጠየቅ ስለማይችል የተጠየቀዉ ኪሳራ የህግ መሰረት የለዉም የቤት ኪራይና የሰራተኛ ወጪ ተመላላሽ ታካሚ ከሆነች ከቤቷ ተመላልሳ መታከም ትችል ነበር፤ የገንቢ ምግብ ወጭ የተጋነነ ነዉ ጉዳት ባይደርስም ለምግብ ማዉጣቷ የማይቀር ነዉ፤ ልዩ ልዩ ወጪዎች የተጋነኑ በመሆናቸዉ ተገቢነት የላቸዉም ሲል መልስ ያቀረበ ሲሆን 2ኛ ጣ/ገብም ደምበኛዬ 2ኛ መልስ ሰጭ መኪና ጥፋት ስለሌለበት ልንጠየቅ አይገባም ኃላፊነት አለባቹ ከተባልንም በመድን ዉል መሰረት እስከ ብር 40,000 ብቻ ነዉ በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የአብከመ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመመርመር በከሳሽ ላይ ለደረሰዉ ጉዳት ኃላፊ ሊሆን የሚገባዉ 2ኛ ተከሳሽ በመሆኑ ከሳሽ ለደረሰባት ጉዳት ካሳ ብር 399,177.55 2ኛ ተከሳሽ ሊከፍል ይገባል፣ የመኪና መድን ሽፋን የሰጠዉ 2ኛ ጣ/ገብ በዉላቸዉ መሰረት ለተሽከርካሪዉ በሰጠዉ የመድን ሽፋን መጠን ለደረሰዉ ጉዳት ብር 40,000 የጉዳት ኪሳራ ሊከፍል ይገባል በማለት እና ከሳሽ የወጪ ዝርዝር በ2ኛ ተከሳሽና በ2ኛ ተጠሪ ላይ የማቅረብ መብቷን ጠብቆላት 1ኛ ተከሳሽና 1ኛ ጣ/ገብ ተጠያቂነት የለባቸዉም በማለት ከክሱ በነጻ በማሰናበት ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የአመልካች ቅሬታ በማስረጃ ያልተደገፈ በመሆኑ እና የስር ፍርድ ቤት የዓይን እማኞችን መሰረት በማድረግ ከሶስት ቀን በኋላ የተነሳዉን የተራፊክ ፖሊስ የፕላን ማስረጃ ዉድቅ ማድረጉ የሚነቀፍ አለመሆኑን የሰበር ዉሳኔዎችን ጠቅሶ የስር ፍርድቤትን ዉሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.348/1/ መሰረት አጽንቶታል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም ይህንን የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘት በአጭሩ፤የአደጋው መንስኤ ንብረትነቱ የ1ኛ ተጠሪ የሆነው የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 3-33889 የሆነ ተሽከርካሪ የራሱን ቀኝ መስመር ጥሎ ወደ ተቃራኒ ግራ መስመር 2 ሜትር ከ33 ሳ.ሜ አልፎ ንብረትነቱ የአመልካች የሆነው የሰሌዳ ቁጥር 3-55830 ጋር በመጋጨት አደጋው መድረሱንና ጥፋተኛ መሆኑን ከትራፊክ ጽ/ቤት እና ከተለያዩ ክፍሎች በተጻፈ ደብዳቤዎች እና በአደጋው ጊዜ በተነሳው ፕላን ተረጋግጦ እያለ ማስረጃዎቹን የሚያስተባብል ከሚመለከተው ክፍል ማስረጃ ሳያቀርቡ የስር ፍ/ቤት 1ኛ ተጠሪ እና 3ኛ ተጠሪ ኃላፊነት የለባቸውም በማለት የሰጠው ውሳኔ መጽናቱ ተገቢ አለመሆኑን፤ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2084/1/ ሁለት ባለሞተር ተሽከርካሪዎች ሲጋጩ እያንዳንዱ ተሽከርካሪ አንዱ በአንዱ ላይ አደጋ እንዳደረሰ ይቆጠራል በሚለው መሰረት ሁለቱ መኪናዎች እርስ በእርሳቸው ተጋጭተው ጉዳት የደረሰ ስለሆነ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ሁለቱም ኃላፊነት ያለባቸው ሲሆን የአንጎለላ ጮራራ መንዲ ፖሊስ በቁጥር 901/ነበ/ጠራ/ወም/22/11 በቀን 10/03/2011 ዓ.ም በጻፈው ደብዳቤ አመልካችና 1ኛ ተጠሪ በጋራ ብር 27,850.00 ህይወታቸው በተሽከርካሪ አደጋ ላለፉት ግለሰቦች ወጪ የከፈሉ በመሆኑ 1ኛ ተጠሪ የጋራ ኃላፊነቱን አምነው እንደተቀበሉ የሚያሳይ ስለሆነ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ የጋራ ኃላፊነት አለባቸው ተብሎ ውሳኔ መሰጠት ሲገባው አመልካች ብቻ ለጥፋቱ ኃላፊ ሆኜ በዉሳኔዉ የተጠቀሰውን ገንዘብ እንድከፍል የተሰጠው ውሳኔ በስር ፍ/ቤት መጽናቱ ተገቢ አይደለም የሚል ነዉ፡፡

የአመልካች አቤቱታ በሰበር ችሎቱ ተመርምሮ የትራፊክ ፖሊስ ፕላንና የሙያ ማስረጃ እንዲሁም ለተለያዩ ክፍሎች የተጻፉት ማስረጃዎች ታልፈዉ ለደረሰዉ አደጋ ኃላፊነት ያለበት አመልካች ነዉ በማለት የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል መዝገቡ ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ታዟል፡፡

1ኛ ተጠሪ ሚያዚያ 07 ቀን 2016ዓ/ም በተጻፈ መልስ አንድ የባለሙያ ማስረጃ በበቂ ማስረጃዎች ሊስተባበል የሚችል መሆኑን ጠቅሰዉ የትራፊክ ፖሊስ ፕላንን በተመለከተ በስር ፍርድ ቤት የአይን እማኞች (የባጃጅ ሹፌር) የነበሩ ጉዳዩን ከመጀመርያ እስክ መጨረሻ የተከታተሉ እና በጊዜዉ ግን ፖሊስ አደጋዉ በደረሰበት ቦታ ላይ ምንም አይነት ምልክት ያላደረገ መሆኑን እና የአደጋዉን ሁኔታ አስረድተዋል በማለት የምስክሮችን የምስክርነት ቃል ዘርዝር አድርገዉ ጠቅሰዋል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅፅ 12 በመ/ቁጥር 14891 እና በመ/ቁጥር 43453 እንዲሁም በቅፅ 24 በመ/ቁጥር 175142 በሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሰረት የባለሙያ አስተያየት በምሰክሮች ቃል የሚስተባበል በመሆኑ እና የ1ኛ መልስ ሰጭ ምስክሮችም የፕላን ማስረጃውን በበቂ ሁኔታ ያስተባበሉልኝ ስለሆነ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ በአግባቡ ነው፡፡ በአመልካች በኩል የቀረበው ፕላን ከዚህ በተጨማሪ ሰዓት እና ቀን የማይገልፅ ለብቻው የተሰራ 1 ገፅ ፕላን ሲሆን መርማሪው በፍርድ ቤት የምስክርነት ቃል ከሰጡ በኋላ ሌሎች ተያያዥ ሰነዶች እንዲቀርቡ ሲታዘዝ ሌላ ገፅ በማዘጋጀት ያቀረቡት ባለንብረቶች ፈርመዋል ሲሉ ያቀረቡት ሰነድ ነው፡፡ ይህ ሰነድ በሌላ ግዜ የተዘጋጀ ሲሆን የአሁን 1ኛ መልስ ሰጭ በፕላን ላይ ተስማምቼ አልፈረምኩም፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተገቢ በመሆኑ ሊፀናልኝ ይገባል ብሏል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

2ኛ ተጠሪ ሚያዝያ 03 ቀን 2016 ዓ.ም አቅርበዋል ይዘቱም ከፊት ለፊቱ መንገድ ላይ የተጋደመን ግንድ ለማለፍ ሲል የራሱን ቀኝ መስመር መጠበቅ ሲገባው ወደግራ መስመር በመግባት የግጭት አደጋው እንዲከሰት ያደረገው እና የአደጋው መንስኤም የአሁን አመልካች ተሽከርካሪ በመሆኑ ግጭቱ ሲከሰት የ1ኛ ተጠሪ መኪና በተፈጠረው ግጭት በአመልካች መኪና ተገፍቶ /ተጎትቶ/ ወደ አመልካች ተሽከርካሪ መስመር መግባቱን በወቅቱ በቅርብ እርቀት ላይ ሆነው ያዩ የነበሩ እማኞች ያስረዱ በመሆኑ በስር ፍርድ ቤት የተፈጸመ የማስረጃ ምዘና ስህተት ባለመኖሩ ዉሳኔዉ እንዲጸናልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

3ኛ ተጠሪ ሚያዝያ 07 ቀን 2016 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርቧል ይዘቱም 1ኛ ተጠሪ በአደጋው ፕላን ላይ መፈረማቸውን እና ውጤቱን በተመለከተ የፖሊስ ንድፉ(ፕላኑ) እንደማንኛውም ማስረጃ በችሎት ተመርምሮ ውድቅ ሊደረግ የሚችል ስለሆነ የስር ፍ/ቤት ከዓይን ምስክሮች በተነገረው ፍሬ ነገር ላይ ተመስርቶ የሰጠው ውሳኔ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 43453(ቅፅ 12) ላይ በሰጠዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት በመሆኑ የሚነቀፍበት ምንም ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ 1ኛ ተጠሪ በሰብዓዊነትም ይሁን በማናቸውም ምክንያት ለተጎዱ ሰዎች ድጋፍ ማድረጋቸው ለደረሰው አደጋ ኃላፊ መሆናቸውን ወይም ማመናቸዉን የማያስረዳ በመሆኑ የቀረበዉ አቤቱታ የህግ መሰረት የለዉም፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ የሚነቀፍ እና መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም ስለሆነም ሊጸና ይገባል ሲሉ አመልካችም አቤቱታቸዉን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና የክርክሩ ይዘት በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን ይህ ችሎትም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አኳያ እና ከተገቢው ህግ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነዉም በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ) ላይ በግልጽ እንደተመለከተዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉን ዉሳኔዎች በማረም ላይ የተገደበ ነዉ፡፡ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ትርጓሜ ይሰጣል፡፡ በአዋጁ በትርጉም ክፍል አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለዉ አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን፣ ህግ ያላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉን ህግ የሚጠቅስ፣

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ለክርክሩ አግባብነት ያለዉ ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለዉ ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፣ በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ዉድቅ በማድረግ የተወሰነ፣ በፍርድ አፈፃፀም ሂደት ከዋናዉ ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትዕዛዝ የተሰጠበት፣ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተወሰነ፣ የአስተዳደር አካል ወይም ተቋም ከህግ ዉጭ የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ በመቃረን የተወሰነ ሲሆን ነዉ።

በተያዘው ጉዳይ ለካሳ ክርክሩ ምክንያት የሆነው የተሽከርካሪ አደጋው ሊደርስ የቻለው በአመልካች ተሽከርካሪ አሽከርካሪ ጥፋት መሆኑን ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ተቀብለው ወስነዋል። በአንጻሩ የትራፊክ ባለሙያ ምስክርነትና በሰነድም የቀረበው የትራፊክ ፕላን ይህን የሚያሳይ አይደለም የሚለው የአመልካች ቀዳሚ መከራከሪያ ነው። በአደጋው ቦታ በነበሩ ቀጥተኛ ምስክሮች እና በትራፊክ የሙያ ማስረጃ መካከል ልዩነት በመኖሩ ይግባኝ ሰሚ የጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የትኛው ማስረጃ ተቀባይነት እንዳለው መዝነዋል። ምስክሮች በአደጋው ወቅት ቦታው ላይ የነበሩ እና ቀጥተኛ ማስረጃ በመሆናቸው፤ የትራፊክ ባለሙያ ግን ፕላን ያነሳው ከአደጋ በኂላ (ከ3 ቀን በኃላ) በመሆኑ ቀጥተኛ ማስረጃ ባለመሆኑ በቦታው የነበሩ ምስክሮች ቃል ተቀባይነት ያለው አሳማኝ ማስረጃ ነው የሚል መደምደሚያ ላይ ተደርሷል። የባለሙያ ማስረጃ በሌላ ማስረጃ ሊስተባበል የሚችል ማስረጃ መሆኑን የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰበር መ/ቁጥር 43453 (በቅጽ 12 እንደታተመው) እና በሌሎች መዝገቦች የህግ ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ ነው። በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አደጋዉ የደረሰዉ በአመልካች ተሽከርካሪ ጥፋት መሆኑ ከምስክሮች ቃል የተረጋገጠ በመሆኑ ለጉዳቱ ሃላፊነት ያለበት አመልካች ብቻ ነው በማለት የደረሰበት መደምደሚያ እና በፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይህንኑ በማጽናት የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የማስረጃ ምዘና መርህን በመከተል ውሳኔ መሰጠቱን የሚያሳይ በመሆኑ በማስረጃ ምዘና ረገድ የፈጸሙት መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም። ከፍሲል እንደተገለፀው ይህ ሰበር ችሎት የህገ ስህተት ማረም እንጂ ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ስለሌለው ይግባኝ ሰሚ ችሎቶች የደረሱበትን መደምደሚያ ይህ ችሎት የሚቀበለው ነው።

በአጠቃላይ ከፍ ሲል በተጠቀሰው መልኩ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ያሳለፉት ውሳኔ በማስረጃ ምዘና ስልጣናቸው ተረጋገጠ ያሉትን ፍሬ ነገርና ህጉን መሠረት ያደረገ ነው ከሚባል በስተቀር ውሳኔው በዚህ ሰበር ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚባል ሆኖ አላገኘነውም። ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል።

## ው ሳ ኔ

1. የአማራ ብ/ክ/መ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 01-21402 ታህሳስ 22 ቀን 2014 ዓ/ም እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 221959 ግንቦት 25 ቀን 2015 ዓ/ም የሰጡት ዉሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በስር ፍርድ ቤት የተጀመረው አፈፃፀም ታግዶ እንዲቆይ የተሰጠ ትእዛዝ ካለ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
3. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የሰበር መዝገብ ቁጥር 251014
ጥቅምት 7 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች፡- ወ/ሮ ራጂ ገመቹስ ጠበቃ አቶ ሽፈራው አመኑ ቀርቧል

ተጠሪ፡- አቶ ቦጃ ተስፋዬ አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ጉዳዩ የባልና ሚስት ንብረት ክርክር የሚመለከት ሲሆን አመልካች እና ተጠሪ መጋቢት ወር 2006 ዓ.ም ጋብቻ መስርተው ሲኖሩ ትዳራቸው መጋቢት 13 ቀን 2014 ዓ.ም በመዝገብ ቁጥር 2020/26257 በኖርዌይ ሀገር በፍርድ ቤት በተላላፈ የፍቺ ውሳኔ መፍረሱን ተከትሎ ከተጠሪ ጋር በጋራ አፈራናቸው ያሏቸውን ንብረቶችን ዘርዝረው የሚስትነት ድርሻቸው እንዲወሰንላቸው ለፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዳኝነት ከጠየቁባቸው ንብረቶች መካከል ለሰበር ቅሬታው ምክንያት የሆነው በተጠሪ ስም በኦሮሚያ ባንክ አ.ማ ያለ አክሲዮን እና በአሮሚያ ባንክ በተጠሪ ስም በተከፈተ ሂሳብ ቁጥር ተቀማጭ የሐኑ ገንዘብ ይገኝበታል፡፡ ተጠሪ እነዚህን ንብረቶች በተመለከተ ባቀረቡት መልስ፡- አመልካች በአሮሚያ ባንክ በተጠሪ ስም በተከፈተ ሂሳብ ቁጥር ተቀማጭ የሐነውን 1,200,000.00(አንድ ሚልዮን

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ሁለት መቶ ሺ) ብር በተመለከተ ግራ ቀኙ በኖርዌይ ሀገር ፍርድ ቤት በኢትዮጵያ አቆጣጠር መስከረም 29 ቀን 2013 ዓ.ም የመለያየት ውሳኔ ተሰጥቶ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ተለያይተው የኖሩ ሲሆን የመለያየት ውሳኔው ከተሰጠ በኋላ የተፈሩ ንብረቶች የግል በመሆኑ ከአመልካች ጋር ከተለያዩ በኋላ በስማቸው በተከፈተ የሂሳብ ቁጥር ተቀማጭ የሖነው ገንዘብ የግላቸው ስለሆነ አመልካች ሊካፈሉ የሚገባው የመለያየት ውሳኔው ሲሰጥ በሂሳብ ቁጥራቸው መኖሩ የተረጋገጠውን 46,404.43(አርባ ሲድስት ሺ አራት መቶ አራት ከ43/100) እንጅ 1,200,000.00(አንድ ሚልዮን ሁለት መቶ ሺ) ብር አለመሆኑን ፤ በኦሮሚያ ባንክ አ.ማ በተጠሪ ስም ያለውን አክሲዮን የተገዛው ከአመልካች ጋር ጋብቻ ከመፈጸማቸው በፊት በመሆኑ የግል ንብረታቸው መሆኑን ተከራካረዋል፡፡ በክስ መስማት ወቅት የግራ ቀኙ ጋብቻ መጋቢት 13 ቀን 2014 ዓ.ም ከመፍረሱ በፊት ከተጠሪ ሂሳብ ቁጥር አመልካች ያሸሹት ገንዘብ የጋራ ተብሎ እንዲወሰንላቸው ፤ በኦሮሚያ ባንክ አክስዮን ማኅበር ያለው አክስዮን ከትዳር በፊት የተገዛ ቢሆንም በሂደት የተገኘው አክስዮን የጋራ እንዲባልላቸው አመልካች ተከራካረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ እንዲሁም ተገቢ ነው ያለውን ማጣራት አድርጎ በሰጠው ውሳኔ በአሮሚያ ባንክ አ.ማ በተጠሪ ስም የተመዘገበው አክሲዮን የተገዛው ታህሳስ 25 ቀን 2000 ዓ.ም መሆኑንና በወቅቱ የነበረው የአክስዮን ብዛት 3,251(ሶስት ሺ ሁለት መቶ ሃያ አምስት) መሆኑን መግለጫ ከአክስዮን ማኅበሩ መቅረቡን ጠቅሶ አመልካችና ተጠሪ ትዳር የመሰረቱት ጥር 4 ቀን 2006 ዓ.ም መሆኑን ስላልተካደ አክስዮኑ ግራ ቀኙ ትዳር ከመመስረታቸው ከ6(ስድስት) ወር በፊት ስለተገዛ የተጠሪ የግል ንብረት መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ በትዳር ውስጥ ያለውን የአክስዮን ዕድገት እና የአክስዮኑን ትርፍ በተመለከተ ድርሻ አለኝ የሚል በመሆኑ ከትዳር በፊት የተፈራው አክስዮን በሂደት ካሳየው ዕድገት አመልካች ድርሻ የሌላቸው በመሆኑና ከአክስዮኑ የተገኘውንም ትርፍ ግራ ቀኙ በትዳር ውስጥ እያሉ ለትዳር ጥቅም እንደዋለ የህግ ግምት የሚወሰድበት በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበው ዳኝነት ተቀባይነት የለውም፡፡ በኖርዌይ ሀገር የመለያየት ውሳኔ ከተሰጠበት ከመስከረም 29 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ አመልካች እና ተጠሪ ተለያይተው የኖሩ በመሆኑ ተለያይተው መኖር ከመጀመራቸው በፊት በኦሮሚያ ባንክ በተጠሪ ስም በተከፈተው የሒሳብ ቁጥር መኖሩ የተረጋገጠውን 46,404.43(አርባ ሲድስት ሺ አራት መቶ አራት ከ43/100) የጋራ በመሆኑ ግራ ቀኙ እኩል እንዲካፈሉ፣ ከዚህ ውጭ ያለው ገንዘብ የተጠሪ የግል ንብረት ነው በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን አከራካሮ በሰጠው ውሳኔ የሥር የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ቤት በኦሮሚያ ባንክ ያለው አክሲዮን ግራ ቀኙ ጋብቻ ከመፈጸማቸው በፊት የተገዛ በመሆኑ አክሲዮኑ የተጠሪ የግል ንብረት ነው ማለቱ የሚነቀፍ አይደለም በማለት ሲያፀና ከአክሲዮኑ የተገኘ መሆኑ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የተረጋገጠውን ትርፍ ብር 721,989.51(ሰባት መቶ ሃያአንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ከ51/100) ብር ለትዳር ጥቅም እንደዋለ ይቆጠራል መባሉ የማስረጃ ምዘና ስህተት አለበት በማለት ገንዘቡ የጋራ ስለሆነ ግራ ቀኙ እኩል ይካፈሉ በማለት ወስኗል፡፡ ተጠሪ ከፍቺ በኋላ ከነበራቸው ብር ላይ ለአቶ ገለታ እምሩ ያስተላለፉት ብር 1,200.000(አንድ ሚልዮን ሁለት መቶ ሺ) የግራ ቀኙ መሆኑን አመልካች ስላላስረዱ የግል ንብረታቸው ነው መባሉ የሚነቀፍ አይደለም በማለት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔን አሻሽሏል፡፡ የሰበር ቅሬታው የቀረበው የስር ፍርድ ቤቶች በተጠሪ ስም በኦሮሚያ ባንክ ተቀማጭ የነበረው ብር 1,200.000(አንድ ሚልዮን ሁለት መቶ ሺ) እና በኦሮሚያ ባንክ አ.ማ ተጠሪ ከጋብቻ በፊት የገዙት አክስዮን ግራ ቀኙ በትዳር ውስጥ እያሉ ያሳየው ዕድገት የተጠሪ የግል ንብረት ነው መባሉን በመቃወም ነው፡፡

የሰበር ቅሬታው በአጭሩ፡- ተጠሪ አመልካችን በ2003 ዓ.ም ከማግባታቸው በፊት በ2000 ዓ.ም የእያንዳንዱ ዋጋ 1,000.00 (አንድ ሺሕ) ብር የሆነ 10(አስር) አክስዮን በ10,000.00 (አስር ሺህ) ብር ገዝተው ብር 500.00(አምስት መቶ) አረቦን/ፕሪሚየም ከፍለው ከአክስዮኑ በየአመቱ ከሚገኘው ትርፍ አክስዮን እየተገዛበት (ካፒታላይዝ) እየተደረገ የአክስዮን መጠኑ አድጎ 3,251.00 (ሶስት ሺ ሁለት መቶ ሃያ አምስት) የደረሰ ሲሆን ፤ በገንዘብ ደግሞ ብር 3,251,000.00(ሶስት ሚልዮን ሁለት መቶ ሃምሳ አንድ ሺ) መድረሱን የኦሮሚያ ባንክ አ.ማ ለሥር የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በላከው ደብዳቤ ተረጋግጧል፡፡ ይህ አክስዮን ከ2000 ዓ.ም እስከ 2003 ዓ.ም እጥፍ አደገ እንኳን ቢባል የአክስዮን መጠኑ ሊሆን የሚችለው 20 (ሃያ) አክስዮን ሲሆን በገንዘብ ደግሞ 20,000.00 (ሃያ ሺህ) ብር ይሆናል፡፡ ከግምት ባለፈም ትክክለኛውን ቁጥር ከባንኩ ጠይቆ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ይህ አክስዮን የጋራ መሆኑ ተረጋግጦ ከዚህ አክስዮን የተገኘው ትርፍ ብር 721,989.51 (ሰባት መቶ ሃያ አንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ 51/100) የጋራ ነው ተብሎ አመልካችና ተጠሪ እኩል እንዲካፈሉ ይገባኝ ሰሚው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ትርፉ የጋራ ነው ተብሎ ተወስኖ የትርፉ ምንጭ የሆነው አክስዮን የግል ነው መባሉ የቤተሰብ ሕጉን አንቀጽ 62 ድንጋጌን የጣሰ እና መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ግድፈት የተፈፀመበት ነው ፤ እንዲሁም የኦሮሚያ ባንክ አ.ማ ለፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በጻፈው ደብዳቤ እና በላከው የባንክ ስቴትመንት ጋብቻው ፀንቶ እያለ ብር 1,200,000.00 በተጠሪ ስም ተመዝግቦ መገኘቱን ፤ ጋብቻው ፈርሶ የንብረት ክፍፍል ከመደረጉ በፊት ተጠሪ ይህንን ገንዘብ ለአቶ ገለታ እምሩ ማስተላላፋቸው የተረጋገጠ ሲሆን ይህ ተግባር የንብረት ማሸሸ ድርጊት ሆኖእያለ ይህ ገንዘብ የግል ንብረት ለመሆኑ ክርክርም ሆነ ማስረጃ ሳይቀርብ ገንዘቡ የተጠሪ የግል ንብረት ነው ተብሎ በሁለቱም የሥር ፍርድ ቤቶች መወሰኑ ከቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 62 አድማስ ውጪ በመሆኑ የሰበር አቤቱታ ከቀረበባቸው ንብረቶች አንፃር የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ በኦሮሚያ ባንክ አ.ማ ያለው አክሲዮን እና ለአቶ ገለታ እምሩ የተላለፈው ገንዘብ የአመልካች እና የተጠሪ የጋራ ንብረት ነው ተብሎ እንዲወሰን ጠይቀዋል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 6/1 መሠረት ለሰበር ሰሚው ችሎቱ የተመራው የሰበር አቤቱታ በሰበር ሰሚ ችሎቱ ተመርምሮ በግራ ቀኙ መካከል የነበረው የመለያየት ሆነ የፌች ውሳኔ የተሰጠው በኖርዌይ ሀገር ፍርድ ቤት ሲሆን የጋራ ንብረት ክፍፍል ዳኝነት ደግሞ የቀረበው በኢትዮጵያ ፍርድ ቤት በመሆኑ የፍቺ ውጤት ሊዳኝ የሚገባው በየትኛው ሀገር የቤተሰብ ሕግ እንደሆነ፤እንዲሁም በውጭ ሀገር ፍርድ ቤት የተሰጠ የመለያየት ውሳኔ በንብረት ረገድ ስለሚኖረው ውጤት ለመመርመር ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ በሰጡት መልስ፡- የግራ ቀኙ ጋብቻ እና ፍቺ በኖርዌይ ሀገር የተፈፀመ ቢሆንም አከራካሪዎቹ ንብረቶች በኢትዮጵያ ውስጥ ስለሚገኙ በአመልካች እና ተጠሪ ያፈሩት ሀብት እና ንብረት በሚገኝበት ሀገር ተፈፃሚነት ባለው ሕግ ለመዳኘት ምርጫቸው በመሆኑና ይህንን ምርጫቸውን ማክበር በተሸለ መልኩ መብት እና ጥቅማቸውን የሚያስጠብቅላቸው በመሆኑ ችሎቱ ይህንን ፍላጎታቸውን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የሥር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ እንዲያፀናላቸው ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪ ብር 1,200,000.00 /አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺ ብር ኦሮሚያ ባንክ በሚገኘው የባንክ አካውንታቸው ያስገቡት የግራ ቀኙ ጋብቻ ከፈረሰ በኋላ ሲሆን በአንፃሩ ጋብቻቸው እስከፈረሰበት ጊዜ ድረስ በዚሁ አካውንት የነበራቸው የገንዘብ መጠን ብር 46,406.43 /አርባ ስድስት ሺ አራት መቶ ስድስት ብር ከ43/100/ ብቻ በመሆኑ ተጠሪ ከአመልካች ጋር የነበራቸው ጋብቻ ከፈረሰ በኋላ ያፈሩት ገንዘብ የግላቸው እንጂ ከአመልካች ጋር የጋራ ሀብት ሊሆን የሚችልበት የሕግ መሰረት ካለመኖሩም በላይ አመልካች ይህ ገንዘብ ወደ ተጠሪ የባንክ አካውንት የገባው ጋብቻው ፀንቶ በነበረበት ወቅት እንደሆነ ያቀረቡት ክርክር ሀሰት በመሆኑ በሥር ፍርድ ቤቶች በማስረጃ የተረጋገጠ መሆኑን ገልጸው ያቀረቡት ቅሬታም ተቀባይነት የለውም፡፡ በኦሮሚያ ባንክ አ.ማ ያለውን አክሲዮን ተጠሪ የገዙት አመልካችና ተጠሪ ጋብቻ ከመፈፀማቸው በፊት እንደሆነ የተረጋገጠ ሲሆን ተጠሪ ከጋብቻ በፊት ከባንኩ የገዙት የአክሲዩን ብዛት ከ20 አክሲዮን እንዳማይበልጥ አመልካች በግምት የገለጹት ሀሰት በመሆኑና ተጠሪ ከ2000 ዓ.ም በኋላም በየአመቱ በርካታ አክሲዮኖችን ገዝተው እያለ ከጋብቻ በፊት እና ከጋብቻ በኋላ ያለውን የአክሲዮኑን ብዛት ነጥለው በመግለፅ አመልካች ያቀረቡት ክርክር በሥር የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያልቀረበ አዲስ ክርክር በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 329/1/ ድንጋጌ መሰረት ውድቅ ሊደረግ ይገባል፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶች አክሲዮኑ ከጋብቻ በፊት የተገዛ መሆኑን በማስረጃ በማረጋገጥ የወሰኑ በመሆኑና ሰበር ሰሚ ችሎቱ ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ስለሌለው የአመልካች የሰበር ቅሬታ ውድቅ ነው፡፡ ከጋብቻ በፊት በተጠሪ የተገዛ የባንክ አክሲዮን ትርፍ ድርሻ በግራ ቀኙ የጋራ ጥረት ያልተገኘ እና ከጋራ ሀብታቸው /ገንዘባቸው/ ጋር የመቀላቀል ዕድል የሌለው በመሆኑ ከአክሲዮኑ የተገኘው ትርፍ የሁለቱ የጋራ ሀብት ሊሆን አይችልም፡፡ አንድ ንብረት የጋራ የሚያሰኘው በተጋቢዎች የጋራ ጥረት በጋብቻ ውስጥ የተፈራ መሆኑ የተረጋገጠ ከሆነ ብቻ በመሆኑ አመልካች ለአክሲዮን እድገቱ ያደረጉት አስተዋፅኦ መኖሩ ባልተጋገጠበት ሁኔታ አክሲዮኑ የጋራ ይባልልኝ

በማለት ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት ስለሌለው በዚህ ረገድ የቀረበው ቅሬታ ውደቅ ሆኖ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንዲጸናላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም ባቀረቡት የመልስ መልስ ከዓለም አቀፍ የግለሰብ ሕግ (Private International Law) አንፃር የችሎቱ ማስቀረቢያ ጭብጥ ላይ በተጠሪ የቀረበውን መልስ እንደሚቀበሉ ገልፀው የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክዋል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለ መልኩ የተመለከተው የግራ ቀኝ ክርክር እና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡት ውሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አንድ ጉዳይ የግል ዓለም አቀፍ ሕግ ተፈጻሚነት /conflict of laws/ የሚያስነሳ ነው ሊባል የሚችለው አንድን ጉዳይ የሚገዙት ለክርክሩ አወሳሰን አግባብነት ያላቸው የተለያዩ አገሮች ሕጎች ክርክሩ በተለያየ አግባብ እንዲፈታ የሚደነግጉ መሆኑ ሲረጋገጥ ፣ በዚህም ምክንያት የተለያዩ አገሮች ሕጎች ግጭት ወይም ተቃርኖ /conflict of laws/መኖሩ ሲረጋገጥ እና ከእነዚህ የተለያዩ አገሮች ሕጎች መካከል ክርክሩ ሊወሰን የሚገባው በየትኛው አገር ሕግ መሰረት ነው? የሚል ጥያቄ አከራካሪ ሆኖ ሲቀርብ መሆኑን የግል ዓለም አቀፍ ሕግ አጠቃላይ መርሆዎች ያመለክታሉ፡፡ የግል ዓለም አቀፍ ሕግ ተፈጻሚነት /conflict of laws/ በሚያስነሳ ጉዳይ ተከራካሪዎች በክርክራቸው አግባብነት ያለው ሕግ መምረጥ የሚችሉ ቢሆንም ይህ ተከራካሪዎች ለጉዳያቸው ተፈፃሚነት ያለው ሕግ የመምረጥ ነፃነት እንደጉዳዩ ዓይነት(types of case)፣የፍርድ ቤት ሥልጣን(jurisdiction)፣የህዝብ ፖሊስ (public policy) እና በሕግ ሊገደብ ይችላል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት የኢትዮጵያ አሠርና ሠራተኛ ሕግ የመንግስት ፍላጎት የሚንፀባረቅበት ሕግ በመሆኑ ተፈፃሚነት እንዳይኖረው የሚደረግ ስምምነት ተቀባይነት እንደሌለው በሰበር መዝገብ ቁጥር 54121(በቅጽ 11 እንደታተመው ገጽ 545) አስገዳጅ ውሳኔን ሰጥቷል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ከክርክሩ መገንዘብ እንደተቻለው አመልካችም ሆኑ ተጠሪ የኖርዌይ ዜግነት ያላቸው ሆነው በ2006 ዓ.ም ጋብቻ መስርተው ሲኖሩ የነበሩት፣የመለያየት እና የፌቺ ውሳኔ የተሰጠው በኖርዌይ ሲሆን የፍቺ ውጤት የሆነው የንብረት ክርክር የቀረበው እና አከራካሪዎቹ ንብረቶች ያሉት በኢትዮጵያ ውስጥ መሆኑ፣የግራ ቀኙ የዜግነት አገር ሕግ፣ የመደበኛ መኖሪያ አገር ሕግ፣ጋብቻው የተፈፀመበት አገር ሕግ፣ክርክሩ የቀረበበት አገር ሕግ፣ለክርከሩ ምክንያት የሖነው ንብረት የሚገኝበት አገር ሕግ፣እንዲሁም ተከራካሪ ወገኖች የተስማሙበት አገር ሕግ የተፈፃሚነት ጉዳይ ስለሚያስነሳ አከራካሪ ሆኖ ለቀረበው የዳኝነት ጥያቄ ውሳኔ ለመስጠት ደግሞ የእነዚህ ሀገሮች ሕጎች ለክርክር የቀረበውን ጉዳይ የሚፈቱበትን አግባብ መለየትን፣ለክርክር የቀረበውን ጉዳይ በመፍታት ረገድ በእነዚህ ሀገሮች ሕጎች መካከል አለመጣጣም (Conflict) መኖር አለመኖሩን መለየትን፣አለመጣጣም

የሚኖር ከሆነ አለመጣጣሙ የሚፈታበትን አግባብ መለየትን እና በመጨረሻም ለጉዳዩ አወሳሰን አግባብነት ያለውን ሕግ መምረጥን ስለሚጠይቅ በግራ ቀኙ መካከል የነበረው የመለያየት ሆነ የፌች ውሳኔ የተሰጠው በኖርዌይ ሀገር ፍርድ ቤት ሆኖ የጋራ ንብረት ክፍፍል ዳኝነት የተጠየቀው በኢትዮጵያ ፍርድ ቤት በመሆኑ የፍቺ ውጤት ሊዳኝ የሚገባው በየትኛው ሀገር ሕግ እንደሆነ፤ እንዲሁም በውጭ ሀገር ፍርድ ቤት የተሰጠ የመለያየት ውሳኔ በንብረት ረገድ ስለሚኖረው ውጤት ለመመርመር ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ የተደረገ ቢሆንም ተጠሪ ለሰበር አቤቱታው በሰጡትም መልስ የግራ ቀኙ ጋብቻ እና ፍቺ በኖርዌይ ሀገር የተፈፀመ ቢሆንም አከራካሪዎቹ ንብረቶች በኢትዮጵያ ውስጥ ስለሚገኙ በአመልካች እና ተጠሪ ያፈሩት ሀብት እና ንብረት በሚገኝበት ሀገር ተፈፃሚነት ባለው ሕግ ለመዳኘት ምርጫቸው በመሆኑና ይህንን ምርጫቸውን ማክበር በተሻለ መልኩ መብት እና ጥቅማቸውን የሚያስጠብቅላቸው በመሆኑ ችሎቱ ይህንን ፍላጎታቸውን ከግንዛቤ ውስጥ እንዲያስገባላቸው የጠየቁ ሲሆን አመልካችም በመልስ መልስ ክርክራቸው ከዓለም አቀፍ የግለሰብ ሕግ (Private International Law) አንፃር የችሎቱ ማስቀረቢያ ጭብጥ ላይ በተጠሪ የቀረበውን መልስ እንዲምቀበሉ ስለገለጹ እና ተጠሪም በተያዘው ጭብጥ ላይ ሳይሆን የሰበር አቤቱታውን መሠረት አድርጎ መልስ ስለሰጡ በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 7/6 መሠረት በተለወጠው ጭብጥ ላይ መልስ እንዲሰጡበት ማዘዝ አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በሌላ በኩል አከራካሪውን በተጠሪ ስም በተከፈተ የሒሳብ ቁጥር በኦሮሚያ ባንክ ተቀማጭ የሆነውን 1,200,000.00 /አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺ ብር ውስጥ 46,404.43(አርባ ሲድስት ሺ አራት መቶ አራት ከ43/100) ብቻ እንዲካፈሉ የፌደራል የመጀሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የወሰነው ቀሪው ገንዘብ በኖርዌይ ሀገር የመለያየት ውሳኔ ከተሰጠበት ከመስከረም 29 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ አመልካች እና ተጠሪ ተለያይተው በኖሩበት ጊዜ የተፈራ ነው በሚል ሲሆን ጉዳዩን በይባኝ የተመለከተው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከዚህ ነጥብ አንፃር የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን ውሳኔ ያፀናው የፍቺ ውሳኔ ከተላለፈበት ከመስከረም 29 ቀን 2013 ዓ.ም በኋላ የተፈራ ንብረት ነው በሚል ነው፡፡ አመልካች ያቀረቡት የንብረት ድርሻ ይገባኛል ክስ መጋቢት 13 ቀን 2014 ዓ.ም በመዝገብ ቁጥር 2020/26257 በኖርዌይ ሀገር በፍርድ ቤት የተላላፈን የፍቺ ውሳኔ ተከትሎ ሲሆን ተጠሪም ለክሱ በሰጡት መልስ መስከረም 29 ቀን 2013 ዓ.ም የመለያየት ውሳኔ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ግራ ቀኙ ተለያይተው በሚኖሩበት ጊዜ የተፈራ ንብረት የግል ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ 1,200,000.00 /አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺ ብር ኦሮሚያ ባንክ ያስገቡት የግራ ቀኙ ጋብቻ ከፈረሰ በኋላ በመሆኑ ጋብቻቸው እስከፈረሰበት ጊዜ ድረስ በአመልካች ስም በተከፈተ የሂሳብ ቁጥር ተቀማጭ የሆነው የገንዘብ መጠን ብር 46,406.43 /አርባ ስድስት ሺ አራት መቶ ስድስት ብር ከ43/100/ ብቻ እንዲካፈሉ መወሰኑ አግባብ ነው በማለት ተጠሪ ለሰበር አቤቱታው ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ግራ ቀኙም በችሎት ተጠይቀው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መስከረም 29 ቀን 2013 ዓ.ም የተሰጠውን የፍቺ ውሳኔ መሠረት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አድርጎ ጉዳዩን ማየቱ አግባብ መሆኑን የገለጹ ሲሆን ተጠሪ ለሰበር አቤቱታው በሰጡት መልስ የግራ ቀኙ ጋብቻ እና ፍቺ በኖርዌይ ሀገር የተፈፀመ ቢሆንም አከራካሪዎቹ ንብረቶች በኢትዮጵያ ውስጥ ስለሚገኙ በአመልካች እና ተጠሪ ያፈሩት ሀብት እና ንብረት በሚገኝበት ሀገር ተፈፃሚነት ባለው ሕግ ለመዳኘት ምርጫቸው እንደሆነ የገለጹ ሲሆን ከዓለም አቀፍ የግለሰብ ሕግ (Private International Law) አንፃር የችሎቱ ማስቀረቢያ ጭብጥ ላይ በተጠሪ የቀረበው መልስ በአመልካች በኩልም ተቀባይነት ያለው ሲሆን ይሕ የተከራካሪዎቹ ስምምነት የተሸሻለውን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 መሠረት ያደረገ በመሆኑ ክርክሩን ከተሸሻለው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የቤተሰብ ሕግ አንፃር ማየቱ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ጋብቻ በተጋቢዎቹ ግላዊ ግንኙነት እና ንብረት በኩል ሕጋዊ ውጤት የሚያስከትል በመሆኑ በፍቺ ውሳኔ ቀሪ ከሚሆኑት ውጪ ያለው ሕጋዊ ውጤት በተጋቢዎች ስምምነት ወይንም በፍርድ ቤት ውሳኔ የሚቋጭ ይሆናል፡፡ የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍልን አስመልክቶ ጋብቻ ሲፈፀም ወይንም በፍቺ ወቅት የተደረገ የሚፀና ሕጋዊ ውል በማይኖርበት ጊዜ የባልና ሚስት ንብረት ተጣርቶ የግል የሆነውን ባለንብረቱ የሚወስድ ሲሆን፣ የጋራ የሆነው ንብረት በሕጉ አግባብ ባልና ሚስቱ እንዲካፈሉ የሚወሰን መሆኑን የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 85 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ያመለክታሉ፡፡

በተጋቢዎቹ እጅ ያሉ ንብረቶች በማን ስም ተመዘገቡ የሚለው ከግምት ውስጥ ሳይገባ የጋራ ሀብት እንደሆኑ ስለሚቆጠር የግል ንብረቴ ነው የሚል ተጋቢ የግሉ/ሷ መሆኑን የማስረዳት ግዴታ እንደለበት ወይንም እንደለባት አንቀጽ 63/1 ያመለክታል፡፡ የባልና ሚስት የጋራ የንብረት ባለሀብትነት የሚፈጠረው በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 1258 ላይ እንደተመለከተው በጋራ ባለሀብቶች መካከል በሚደረግ ስምምነት ሳይሆን በሕግ ነው፡፡ ከተሻሻለው የቤተሰብ ሕጉ ቁጥር 62/1 መረዳት እንደሚቻለው ባልና ሚስት በግል ጥረታቸው የሚያፈሩት ንብረት የጋራቸው ነው፡፡ ባልና ሚስት ጋብቻቸውን በሚፈጽሙበት ጊዜ በየግል የነበራቸው ንብረቶች ወይም ከጋብቻ በኋላ በውርስ ወይም በስጦታ በየግላቸው ያገኙዋቸው ንብረቶች የግል ቢሆኑም ከግል ሀብታቸው የሚገኙ ገቢዎች የጋራ ናቸው፡፡( የተሸሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 57 እና 62/1 ይመለከቷል)፡፡ ይህ የሕጉ እሳቤ ጋብቻ በተጋቢዎቹ ግላዊ ግንኙነት ላይ ከሚያስከትላቸው ውጤቶች አንዱ በአንቀጽ 49/1 ሥር የተመለከተው የመተጋገዝና መደጋገፍ ግዴታ መኖር በባልና ሚስት ግንኙነት ውስጥ ከሚፈራው ንብረት ጀርባ የተጋቢዎቹ ጥረት ይኖራል በሚል ግምት መነሻነት ነው፡፡ በዚህ አግባብ በሚፈራው የጋራ ንብረት ላይ ባልና ሚስቱ እኩል መብት ያላቸው መሆኑን ከሕገ መንግስቱ አንቀጽ 34/2 እና የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 90 ድንጋጌ መረዳት ይቻላል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አመልካች እና ተጠሪ 2006 ዓ.ም በኖርዌይ አገር ጋብቻ መስርተው ሲኖሩ መስከረም 29 ቀን 2013 ዓ.ም በተሰጠ የመለያየት ውሳኔ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ተለያይተው ሲኖሩ ቆይተው ትዳራቸው መጋቢት 13 ቀን 2014 ዓ.ም በኖርዌይ ሀገር በፍርድ ቤት በተላላፈ የፍቺ ውሳኔ መፍረሱን ተከትሎ በጋራ የተፈሩ ንብረቶችን ለመካፈል አመልካች ለጠየቁት ዳኝነት ተጠሪ በሰጡት መልስ በኦሮሚያ ባንክ በስማቸው በተከፈተ ሂሳብ ቁጥር ተቀማጭ ከሆነው 1,200,000.00(አንድ ሚልዮን ሁለት መቶ ሺ) ብር ውስጥ የጋራ ሊሆን የሚገባው የመለያየት ውሳኔ ሲሰጥ በሂሳብ ቁጥራቸው መኖሩ የተረጋገጠውን 46,404.43(አርባ ሲድስት ሺ አራት መቶ አራት ከ43/100) ብር ነው በማለት የሚከራከሩ ሲሆን ይህንን ክርክር የሚያቀርቡበት ምክንያት በኖርዌይ ሕግ የመለያየት ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ የሚፈራ ንብረት የግል በመሆኑ ነው፡፡ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 ከፍቺ ውሳኔ በፊት የሚሰጥ የመለያየት ውሳኔ ባለመኖሩ በኖርዌይ ሕግ እና በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ መካከል ግልጽ ተቃርኖ ቢኖርም ግራ ቀኙ በአዋጅ ቁጥር 213/1992 መሠረት ጉዳያቸው እንዲታይ ስለተስማሙ የግራ ቀኙ ጋብቻ በፍርድ ቤት ከመፍረሱ በፊት አመልካች እና ተጠሪ ተለያይተው ስለኖሩ ብቻ የግል ሊሆን የሚችልበት የሕግ አግባብ ባለመኖሩ አመልካች እና ተጠሪ ሲለያዩ በተጠሪ የሂሳብ ቁጥር ተቀማጭ የሆነው 46,404.43(አርባ ሲድስት ሺ አራት መቶ አራት ከ43/100) ብር ብቻ የጋራ ነው መባሉ የቤተሰብ ሕጉን ድንጋጌ መሠረት ያደረገ ካለመሆኑም በላይ ተጠሪ ክርክር የነበረው አከራካሪው ገንዘብ የተፈራው የመለያየት ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ ነው የሚል ሆኖእያለ በይግባኝ እና የሰበር ክርክራቸው ከፌች በኋላ የተፈራ ነው በማለት ካቀረቡት ክርክር ጋር የሚጣረስ ሲሆን የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አከራካሪው ገንዘብ ከፌች በኋላ የተፈራ የተጠሪ የግል ንብረት ነው በሚል የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔን ማጽናቱ በሥር ያልተነሳን ክርክር መሠረት አድርጎ በመሆኑ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉን ቁጥር 329 መሠረት ተቀባይነት የሌለው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ አሁን ላይ ተጠሪ የመለያየት ውሳኔን መሠረት አድርጎ የሚያቀርቡት ክርክር አለመኖሩን ችሎቱ አረጋግጧል፡፡

በሌላ በኩል በኦሮሚያ ባንክ አ.ማ በተጠሪ ስም ያለው አክሲዮን ተጠሪ ከአመልካች ጋር ጋብቻ ከመፈጸማቸው በፊት የተገዛ የግል ንብረታቸው መሆኑ የተከራካሩ ሲሆን አክስዮኑ ከትዳር በፊት የተገዛ ቢሆንም በሂደት የተገኘው አክስዮን የጋራ እንዲባልላቸው አመልካች በክስ መስማት ወቅት ተከራካረዋል፡፡ በኦሮሚያ ባንክ አ.ማ በተጠሪ ስም የተመዘገበው አክሲዮን የተገዛው ታህሳስ 25 ቀን 2000 ዓ.ም መሆንኑና አክሲዮኑ ዕድገት አሳይቶ መግለጫው በቀረበ ጊዜ የነበረው ብዛት 3,251(ሶስት ሺ ሁለት መቶ ሃያ አምስት) መሆኑን ከአክስዮን ማኀበሩ መግለጫ መቅረቡን ከውሳኔ መረዳት ተችሏል፡፡ በተሸሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 57 መሠረት ተጠሪ አመልካችን ከማግባታቸው በፊት የተገዙት አክስዮኖች የግላቸው ቢሆኑም ግራ ቀኙ በትዳር ውስጥ እያሉ አክስዮኑ

ማደጉ ተገልጾ እያለ በትዳር ውስጥ የጨመረው የአክስዮን መጠን በአንቀጽ 62/1 መሠረት የጋራ ሆኖ እያለ ብዛቱ ተለይቶ አለመወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ ቀጣዩ ተወስኗል፡፡

**ውሳኔ**

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 306168 ሰኔ 12 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ ፣ ውሳኔ እና ትዕዛዝ ፣ እንዲሁም የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 304192 መጋቢት 6 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ ፣ ውሳኔ እና ትዕዛዝ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ - ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 9(1/ለ) መሠረት **ተሻሽሏል፡፡**
2. በተጠሪ ስም በኦሮሚያ ባንክ አ.ማ ያለ አክሲዮን እና በአሮሚያ ባንክ በተጠሪ ስም በተከፈተ ሂሳብ ቁጥር ተቀምጦ ከነበረው ገንዘብ ውጪ ያሉ ንብረቶችን በተመለከተ የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ አልተነካም(ፀንቷል)፡፡
3. በአሮሚያ ባንክ በተጠሪ ስም በተከፈተ ሂሳብ ቁጥር ተቀማጭ ሆኖ የነበረው 1,200,000.00(አንድ ሚልዮን ሁለት መቶ ሺ) ብር የአመልካች እና የተጠሪ የጋራ በመሆኑ ተጠሪ ግማሹን የአመልካችን ድርሻ እንዲያካፍሏቸው ተወስኗል፡፡
4. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በፍርድ የዘጋውን የመዝገብ ቁጥር 304192 በማንቀሳቀስ በተጠሪ ስም በኦሮሚያ ባንክ አ.ማ ያለ አክሲዮን ግራ ቀኙ በጋብቻ ውስጥ እያሉ ያደገው የአክስዮን መጠን ምን ያህል እንደሆነ አጣርቶ ሕጋዊ ውሳኔ እንዲሰጥ መዝገቡ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት ቁጥር 17/2015 ቁጥር 9/2 መሠረት ተመልሶለታል፡፡
5. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የግላቸውን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ውሳኔ አግኝቶ ስለተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ/ጋ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁጥር 251074

ጥቅምት 07 ቀን 2017ዓ/ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

ሐብታሙ እርቅይሁን

አመልካች፡- አሊ እጅጉ -ጠ/ማስረሻ በላይ -ቀረቡ

ተጠሪ፡- ሼህ መሐመድ እጅጉ -አልተጠራም

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በዚሁ አግባብ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሐምሌ 19 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 0113178 ግንቦት 16 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 0338977 ሠኔ 13 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ ውርስን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በደሴ ዙርያ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር አመልካች ከሳሽ፣ በዚህ የሰበር ክርክር የሌሉ አቶ ይመር እጅጉ የተባሉ ግለሰብ 1ኛ ተከሳሽ ተጠሪ ደግሞ 2ኛ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

*አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- ወላጅ አባታችን አቶ እጅጉ ይመር ከዚህ አለም በሞት በመለየቱ ምክንያት በዚሁ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 0136147 ወራሽነታችንን አረጋጠናል፣ ተጠሪና የስር 1ኛ ተከሳሽ ከአባቴ በውርስ ማግኘት የሚገባኝን የውርስ መሬቶችና ተንቀሳቃሽ ንብረቶች ይዘዋል፤ አመልካች እኩል እንድንካፈል ብጠይቃቸውም ሊያካፍሉኝ ፈቃደኛ አይደሉም፤ ስለሆነም በክሱ ከ1-33 አዋሳኛቸው የተገለጹትን መሬቶች፤ በተጨማሪም ግምታቸው ብር 46981 / አርባ ስድስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰማንያ አንድ / የሚያወጡ 2 የቆርቆሮ ቤት፤ አንድ በሬ አንድ ላም፤ አንዲት ጊደር፤ አንድ ጥጃ፣ አንድ አህያ እና 4 በጎች እንዲያካፍሉኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡*

*የስር 1ኛ ተከሳሽ በሰጡት መልስ በተራ ቁጥር 27፤ 28 እና 33 የተጠቀሱት መሬቶች በድልድል ከአባቴ ጋር በ1986 ዓ.ም ተካፍዬ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ያወጣሁባቸው በስሜ የሚገኙ መሬቶች ናቸዉ፣ ላም እና ጥጃ የግሌ ናቸው፤ 50 ቆርቆሮ ቤት አንድ ፎቅና ምድር ቤት ያለው አባቴ በሕይወት እያለ ፈቅዶልኝ በይዞታው ላይ የሰራሁት የግል ቤቴ ነዉ በማለት ተከራክረዋል፡፡*

*ተጠሪ በበኩላቸው በሰጡት መልስ ሟች አባቴ በሕይወት እያለ በክሱ ከተገለጹ መሬቶች ውስጥ 15 ለተለያየ ጥቅም የሚውሉ መሬቶችን በቁም ኑዛዜ ሰጥቶኝ በአዋጅ ቁጥር 133/98 መሰረት ተመዝግቦ ለኔ ተላልፈውልኛል፣ 1 ቆርቆሮ ፎቅ እና ምድር ቤትም በኑዛዜ ለእኔ የሰጠኝ በመሆኑ አመልካች በእነዚህ ንብረቶች ላይ ክስ የማቅረብ መብትና ጥቅም የላቸውም በማለት የመጀመርያ ደረጃ መቃወምያ ያቀረቡ ሲሆን በፍሬ ነገሩ ላይ በሰጡት መልስ የሟች አባታችንን ይዞታ በ1986 ዓ.ም ለአቅመአዳም ስንደርስ ግራ ቀኛችንና አባታችን ለአራት ተካፍለን በየስማችን የይዞታ ማረጋገጫ ያሰራን ሲሆን የተጠሪና የአባታችን ድርሻ በአባታችን ስም ደብተር እንዲሰራ ተደርጎ ሟች አባታችን በሕይወት እያለ ድርሻውን ለተጠሪ በኑዛዜ ያስተላለፈልኝ በመሆኑ አመልካች ያካፍሉኝ በማለት ያቀረቡት ጥያቄ ተገቢነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡*

*ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ምስክሮች ከሰማ በኋላ አመልካች የሟች ወራሽ መሆኑን ያረጋገጠ በመሆኑ በመሬቶቹ ላይ መብትና ጥቅም አለው፤ ግራቀኙ የሚከራከሩባቸው መሬቶች የሟች እጅጉ ይመር ናቸው፤ ሟች በሕይወት በነበሩበትት ወቅት ለግራቀኙ የየድርሻቸውን ከፍለው የሠጡ ሲሆን ቀሪውን የራሳቸውን ድርሻ ለተጠሪ በኑዛዜ አስተላልፈዋል፤ የመሬት ባለይዞታ መሬቱን በግብርና ስራ ለሚተዳደር ለሚፈልገው አካል የማስተላለፍ መብት እንዳለው በክልሉ የገጠር መሬት ሕግ አዋጅ ቁጥር 133/98 እና በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 17 ላይ የተደነገገ በመሆኑ ተጠሪ ለአመልካች መሬቶቹን ሊያካፍል የሚችልበት የሕግ ምክንያት የለም፤ የቆርቆሮ ፎቅ ቤትና 1 በሬ ሟች በሕይወት በነበረበት ወቅት ለተጠሪ የሰጠው መሆኑን የቀረቡት ምስክሮች የሰረዱ በመሆኑ እና ሟች መጋቢት 26 ቀን 2009 ዓ.ም ባደረገው የስጦታ ውል የሰጠው በመሆኑ ተጠሪ ለአመልካች ሊሰጥ አይገባም አንድ የቆርቆሮ ፎቅ ቤት እና አንድ ላም ከነጊደሯና ከነጥጃዋ የስር 1ኛ ተከሳሽ የግል ንብረት መሆናቸው በምስክሮች*

*የተረጋገጠ በመሆኑ የስር 1ኛ ተከሳሽ ለአመልካች ሊያካፍለው የሚገባ የውርስ ንብረት የለም ሲል ወስኗል፡፡*

*አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ አንድ የቆርቆሮ ክዳን ፎቅ ቤት እና አንድ ላም የተጠሪ የግል ንብረቶች ለመሆናቸዉ በምስክር ተረጋግጧል፤ የሟች ይዞታ መሬቶች በኑዛዜ ለተጠሪ መተላለፉን የኑዛዜ ሰነዱ ያሳያል፤ ኑዛዜው መሬቱን ብቻ የሚመለከት እንጂ ቤቱን አይመለከትም፤ በሌላ መልኩ ቤቱን በስጦታ የተሰጠው ለመሆኑ ያስረዳልኛል በማለት ያቀረበው የስጦታ ውል በሕጉ አግባብ የተደረገ አይደለም፤ በሬዉን በተመለከተ ስለመስጠቱ የሚገልጽ የጽሁፍ ማስረጃ አልተያያዘም፤ በግ እና ጥጃ ስለመኖራቸዉ ምስክሮች አናዉቅም ብለዋል፤ አንድ አህያ፤ አንደኛዉን ቤት እና አንድ ላም የውርስ ንብረት አለመሆናቸው ተረጋግጧል፤ የእርሻ መሬቱ በሟች አባታቸዉ ኑዛዜ ለተጠሪ የተላለፈ ለመሆኑ የኑዛዜዉ ሰነዱ ያሳያል፤ አመልካች የአባቴ ይዞታዎች ናቸዉ በማለት ከዘረዘራቸዉ መሬቶች ዉስጥ ሶስቱን መሬቶች የስር 1ኛ ተከሳሽ ይዞታ ናቸዉ ያለ ሲሆን ቀሪዎቹን መሬቶች ተጠሪ በኑዛዜ ተላልፎልኛል ብሏል፤ ከዚህም መረዳት የሚቻለዉ ሟች እስኪሞት ድረስ ሲጠቀምበት የነበረዉን ይዞታ መሬቱን በሙሉ ለተጠሪ ያስተላለፈ መሆኑን ነው፣ የሟች ኑዛዜ የሟች ልጅ የሆነዉን አመልካችን ከዉርስ የሚነቅል ነዉ፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 163896 የክልሉ የመሬት ሕግ በግልጽ በሟች የሚደረግ ኑዛዜ አካለ መጠን ያልደረሰን የሟችን ልጅ ከዉርስ መንቀል እንደማይችል የደነገገ ቢሆንም አካለ መጠን የደረሰዉን የሟች ልጅ በተመለከተ በፍትሐብሔር ሕጉ ድንጋጌዎች መሠረት ተፈጻሚ እንደሚሆን በመግለጽ አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፤ የፍትሐብሔር ሕጉ ደግሞ ወደታች የሚቆጠርን ልጅ በዝምታ ከዉርስ መንቀል እንደማይቻል ይደነግጋል፤ በመሆኑም የግራ ቀኙ አባት ይዞታ መሬቱን በሙሉ ለተጠሪ መናዘዙ አመልካችን ከዉርስ የነቀለ በመሆኑ ፈራሽ ነዉ፤ ተጠሪ እና የስር 1ኛ ተከሳሽ የይዞታ መሬቱን፤ አንድ ቤት፤ 1 አህያ እና አንድ በሬ ለአመልካች በድርሻው ሊያካፍሉት ይገባል በማለት የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡*

*ተጠሪ በተራቸው ይህን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ መርምሮ ሟች በሕይወት እያሉ ለአመልካች ጎጆ መውጫ መሬት እንደሰጧቸው በአመልካች አልተካደም፤ ሟች መሬታቸውን ለተጠሪ በስጦታ ያስተላለፉ ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ በመሆኑ የሟች ስጦታ አመልካችን ከውርስ የሚነቅል አይደለም፤ በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 17/3 ላይ ኑዛዜው አካለ መጠን ያልደረሱ የተናዛዡን ልጅ ከውርስ የሚነቅል ሊሆን አይገባም በማለት የተደነገገ ቢሆንም አካለ መጠን የደረሰን ልጅ በተመለከተ ከመሬት ማስተላለፍ ልዩ ባህርይ አንጻር በልዩ ሕግ የሚመራ ነው፤ ከልዩ ሕጉ ድንጋጌ ውጪ በሆነ ሁኔታ አካለመጠን የደረሰን ልጅ ከውርስ ሊነቀል*

አይገባም በማለት በስር ከፍተኛው ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ተገቢነት የለውም፣ በተጠሪ ተይዘዋል የተባሉት የሟች ንብረት የነበሩ አንድ ፎቅ ቆርቆሮ ክዳን ቤትና አንድ በሬን በተመለከተ ሟች በሕይወት እያሉ በስጦታ ለተጠሪ የሰጧቸው ለመሆኑ እንደሚያውቁ የግራ ቀኙ ምስክሮች አስረድተዋል፣ ሟች በሕይወት እያሉ በስጦታ ያስተላለፉትን የማይጠቀሙበትን ንብረት በውርስ ለማስተላለፍ የማይችሉ በመሆኑ እና ተጠሪ የያዘው መሬት በስጦታ በሕጋዊ መንገድ የተላለፈለት ስለሆነ እንዲሁም አንድ ፎቅ ከቆርቆሮ ክዳን ቤት የተሰራ እና አንድ በሬ ሟች በሞት ከመለየታቸው በፊት በስጦታ ለተጠሪ ያስተላለፉ በመሆኑ የውርስ ሐብት ሆኖ ከአመልካች ጋር ሊካፈለው አይገባም ሲል በስር ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡

አመልካች በተራቸው ይህን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም ውሳኔ ሳይለወጥ ቀርቷል፡፡

አመልካች ሐምሌ 19 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይህን ውሳኔ በመቃወም ያቀረበ ሲሆን ይዘቱም፡- ተጠሪና የስር 1ኛ ተከሳሽ የአባታችንን 33 መሬቶች የወሰዱ ስለመሆኑ ባረጋገጡት መሠረት ኑዛዜው አመልካችን ከውርስ የመንቀሉ ጉዳይ ሕጋዊ ነው ወይስ አይደለም ? በማለት እንደ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ጭብጥ በመያዝ ሊወሰን ይገባ ነበር፣ ኑዛዜና ስጦታ ሁለት የተለያዩ ሕጋዊ ተግባራት ናቸው፣ ተጠሪና የስር 1ኛ ተከሳሽ በስር ፍርድ ቤት በተደረገ ክርክር ከአባቴ መሬት እንዳልተሰጠኝ ገልፀዋል፣ አባታችን ሕደር 06 ቀን 2008 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ ተፈጻሚ የሚሆነው አባታችን ከሞተ ከመስከረም 2 ቀን 2015 ዓ.ም በኋላ ነው፣ አባታችን ሳይሞት መጋቢት 16 ቀን 2008 ዓ.ም በኑዛዜ መሰረት መሬት አስተዳደር ለተጠሪ ደብተር ሰርቶ መስጠቱ ከሕግ ውጪ ነው፣ ሟች ለተጠሪ አድርገውታል የተባለው የቤቱ ስጦታ ይዘቱ በማመልከቻ መልክ የተጻፈ ሲሆን የተቀባይ ፊርማ የለበትም፣ ኑዛዜው በሬውን እንደማይመለከት ተረጋግጧል፣ ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እነዚህን ንብረቶች ሟች አባታችን ከመሞታቸው በፊት በሕጋዊ የስጦታ ውል እንደሰጡና ሲሞቱ ንብረቶቻቸው እንዳልነበሩ በማስመሰል የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሻሻለውን የክልሉን የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 17/3 የተረጎመበትና ሰበር ሰሚ ችሎቱም ይህንኑ ትርጉም የተቀበለበት አግባብ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 163896 ከሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ጋር በማገናዘብ ሊመረመር የሚገባው ሆኖ ስለተገኘ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2/4(ሸ) መሠረት ተጠሪ ቀርበው መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

*ተጠሪ ሰኔ 05 ቀን 2016 ዓ.ም በሰጡት መልስ ሟች በሕይወት እያሉ በቁመናቸው ያደረጉት ኑዛዜ ቀደም ብለው ለሌሎቹ ልጆች የሰጡትን ስጦታ ከግምት ውስጥ ያስገባ ነው፤ ሟች በኑዛዜ ለተጠሪው እና ለመጨረሻ ልጃቸው 15 መሬቶችን የሰጡት አመልካች የተጠሪ ታላቅ ወንድም እንደመሆኑ መጠን ወላጅ አባታችን ቀደም ሲል ለጎጆ መውጫና መጠናከሪያ 14 መሬቶች የሰጡት መሆናቸውን በማመዛዘን ነው፣ ሟች በጤናማ አይምሯቸው አንዱን ልጅ ከአንዱ ሳያበላልጡ የሰጡት ኑዛዜ ለሕግና ለሞራል እስካልተቃረነ ድረስ የሚሻርበት አግባብ የለም፣ አመልካች ድርሻቸውን ከወሰዱ በኋላ አሁን ላይ መሬት ያልወሰደ ወይም ምንም መተዳደሪያ የሌለው አስመስሎ ያቀረበው ቅሬታ ቅንነት የጎደለው ነው፤ በስር ፍርድ ቤት ለአዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 17.3 የተሰጠው ትርጉም ሟች ኑዛዜ ሲያስተላልፉ ጥንቃቄ መደረግ ያለበት ከአብራካቸው የተወለደ ለአካለ መጠን ያልደረሰውን ወራሽ ልጃቸውን ከውርሱ መነቀል የለበትም በሚል እንጂ እንደ አመልካች ዓይነቱ ቀድሞ ድርሻውን ተለክቶ ለተሰጠው ወራሽ አይደለም በሚል ነው፤ ስለሆነም ይህንኑ መሠረት በማድረግ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ስለሆነ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡*

*አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡*

*የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸውን ይመስላል፡፡ ይህ ችሎትም ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡*

*ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ባደረጉት ክርክር ሟች አባታቸው በሕይወት እያሉ የሟች አባታችንን ይዞታ ለግራ ቀኞችንና አባታችን ለአራት ተካፍለን በየስማችን የይዞታ ማረጋገጫ ያሰራን ሲሆን የተጠሪና የአባታችን ድርሻ በአባታችን ስም ደብተር እንዲሰራ ተደርጎ ሟች አባታችን በሕይወት እያለ ድርሻውን ለተጠሪ በኑዛዜ እንዳስተላለፉላቸው በመግለጽ የተከራከሩ ሲሆን ሟች በሕይወት በነበሩበትት ወቅት ለግራቀኙ የየድርሻቸውን ከፍለው እንደሰጡ እና ቀሪውን የራሳቸውን ድርሻ ለተጠሪ በኑዛዜ እንዳስተላለፉ በወረዳው ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ፍሬነገር ነው፡፡ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በጭብጥነት የተያዘው እና አከራካሪ የሆነው ጉዳይ ሟች አቶ እጅጉ ይመር ለተጠሪ በኑዛዜ አስተላልፈዋቸዋል የተባሉት መሬቶች ናቸው፡፡*

*የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እነኚህን መሬቶች ተጠሪ ለአመልካች የድርሻቸውን ሊያካፍሏቸው ይገባል ከሚል መደምደሚያ ላይ የደረሰው ሟች እስኪሞት ድረስ ሲጠቀምበት የነበረዉን የይዞታ መሬቱን በሙሉ ለተጠሪ ያስተላለፈ በመሆኑ የሟች ኑዛዜ የሟች ልጅ የሆነዉን አመልካችን ከዉርስ የሚነቅል ነው፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 163896 የክልሉ የመሬት ሕግ በግልጽ በሟች የሚደረግ ኑዛዜ አካለ መጠን ያልደረሰን የሟችን ልጅ ከዉርስ መንቀል እንደማይችል የደነገገ ቢሆንም አካለ መጠን የደረሰዉን የሟች ልጅ በተመለከተ በፍትሐብሔር ሕጉ ድንጋጌዎች መሠረት ተፈጻሚ እንደሚሆን በመግለጽ አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፤*

*የፍትሐብሔር ሕጉ ደግሞ ወደታች የሚቆጠርን ልጅ በዝምታ ከዉርስ መንቀል እንደማይቻል ይደነግጋል በሚል ነው፡፡*

*በአንጻሩ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መሬቶቹን አስመልክቶ የሰጠውን ውሳኔ ሊሽር የቻለው ለአመልካች ጎጆ መውጫ መሬት እንደተሰጣቸው በአመልካችም አልተካደም፤ አካለ መጠን የደረሰን ልጅ በተመለከተ ከመሬት ማስተላለፍ ልዩ ባህርይ አንጻር በልዩ ሕግ የሚመራ ነው በማለት ነው፡፡*

*በኢትዮጵያ ውርስ ሕግ የሟች ውርስ ያለ ኑዛዜ፣ በኑዛዜና በከፊል ኑዛዜና በከፊል ያለ ኑዛዜ የሚፈፀም ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 829 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ የዚሁ ሕግ ቁጥር 938(1)(2) ተናዛዡ ከርስት ከውርስ ለመንቀል የደረሰበትን ምክንያት በኑዛዜው ውስጥ ካልገለጸ በቀር ልጁን ወይም ወደ ታች የሚቆጠር ተወላጆቹን ከውርስ ቢነቅል አይጸናም፤ ተናዛዡ ወራሹን ከውርስ ለመንቀል የሰጠው ምክንያት ትክክል ( እውነት ) እንደሆነ ተቆጥሮ ዳኞች ይህ ምክንያት ከውርስ (ከርስት) ለመንቀል የሚያበቃ መሆን አለመሆኑን ይመረምራሉ በማለት ይደነግጋል፡፡*

*በሌላ በኩል የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 17/1/ የገጠር መሬት ባለይዞታ የሆነ ማንኛውም ሰው የይዞታም ሆነ የመጠቀም መብቱን በግብርና ሥራ ለሚተዳደር ወይም በዚሁ ሙያ ሊተዳደር ለሚፈልግ ሰው በኑዛዜ ማስተልለፍ እንደሚቻል ይደነግጋል፡፡ የዚሁ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር 3 ደግሞ ኑዛዜው አካለመጠን ያላደረሰ የተናዛዡን ልጅ ከውርስ የሚነቅል እና ሕጋዊ የትዳር ጓደኛን መብትን የሚጎዳ ሲሆን ኑዛዜው እንደማይጸና ይደነግጋል፡፡ የዚሁ ሕግ አንቀጽ 54 ደግሞ በአዋጁ ያልተሸፈኑ የገጠር መሬት ኪራይ ስጦታ ውርስ እና ሌሎች ፍትሐብሔር ነክ ጉዳዮችን በተመለከተ እንደነገሩ ሁኔታ አግባብነት ያላቸው የፍትሐብሔር ሕጉ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል በማለት ይደነግጋል፡፡*

*የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 163896 በሰጠው ውሳኔም በአዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 17/3 ድንጋጌ ላይ ኑዛዜው አካለመጠን ያላደረሰ የተናዛዡን ልጅ ከውርስ የሚነቅል እና ሕጋዊ የትዳር ጓደኛን መብትን የሚጎዳ ሲሆን ኑዛዜው አይጸናም በሚል የተገለጸው ሐሳብ አካለመጠን ያላደረሰ ልጅን እና የትዳር ጓደኛን የመብት መጐዳት በኑዛዜ ሰበብ እንዳይደርስባቸው ጥበቃ የማድረግ እንጂ ወራሽ የሆኑ ሰዎች በሕግ ያገኙትን የወራሽነት መብት የሚያሳጣቸው አለመሆኑ፤ በተለይም በአዋጁ አንቀጽ 54 ላይ ውርስን አስመልክቶ በአዋጁ ያልተሸፈኑት ጉዳዮች በፍትሐብሄር ሕጉ እንደሚታዩ መደንገጉ እና ወራሾች በኑዛዜ ከውርስ ንብረት በተነቀሉ ጊዜ እንዴት ሊታይ እንደሚችል በአዋጁ ያልተሸፈነ መሆኑ ሲታይ የፍትሐብሔር ድንጋጌዎችን ተፈፃሚ ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነ በመግለጽ በየትኛውም እርከን ላይ ለሚገኙ ፍርድ ቤቶች አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡*

በያዝነው ጉዳይ ሟች አቶ እጅጉ ይመር ባደረጉት ኑዛዜ ያላቸውን የይዞታ መሬት ለተጠሪ እንዳስተላለፉ እና አካለመጠን የደረሰውን አመልካችን ( ልጃቸውን ) ከውርስ የነቀለ መሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ፍሬነገር ነው፡፡ አመልካች አካለመጠን ያደረሱ በመሆኑ፤ በፍትሐብሔር ሕጉ አግባብ አባታን የመውረስ መብት ያላቸው በመሆኑ እና የይዞታ መሬታቸውን በኑዛዜ ለተጠሪ ያስተላለፉት ሟች አባታቸው አመልካችን ከውርስ የነቀሉበትን ምክንያት በኑዛዜው ላይ ያልገለጹ በመሆኑ አመልካች ለተጠሪ በኑዛዜ ከተላለፉት መሬቶች ውስጥ ድርሻቸውን የማግኘት መብት አላቸው፡፡ ስለሆነም ይህንኑ መሠረት በማድረግ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ሆኖ ሳለ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች ለተጠሪ በኑዛዜ ከተላለፉት መሬቶች ውስጥ ድርሻቸውን ሊወስዱ አይገባም በማለት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

1. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 0113178 ግንቦት 16 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 0338977 ሠኔ 13 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 0113178 ግንቦት 16 ቀን 2015 ዓ.ም ሟች አቶ እጅጉ ይመር ለተጠሪ በኑዛዜ አስተላልፈዋቸዋል የተባሉትን መሬቶች በሚመለከት የሰጠው የውሳኔ ክፍል ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 0338977 ሠኔ 13 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡ ከዚህ ውጪ ያለው የውሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡
3. የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሟች አቶ እጅጉ ይመር ለተጠሪ በኑዛዜ አስተላልፈዋቸዋል የተባሉትን መሬቶች በሚመለከት የሰጠው የውሳኔ ክፍል ጸንቷል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
   - መዝገቡ ውሰኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ም

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 251144

ቀን ፡- ጥቅምት 07 ቀን 2017 ዓ/ም

ዳኞች- እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች፡- አቶ ኤፍሬም አንበሴ -ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ዘመናይ ንጉሴ -ቀረቡ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍርድ**

ጉዳዩ የባልና ሚስት ንብረት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌደራል የመጀመርያ ደረጃ ፍርድ ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት በተደረገ ክርክር አመልካች ተከሳሽ፤ ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- ከአመልካች ጋር የነበራቸው ጋብቻ በፍቺ መፍረሱን ተከትሎ በነባር አጠቃላይ ንግድ አክሲዮን ማሕበር በአመልካች ሥም ከጋብቻ በፊት የነበረው አንድ አክሲዮን ሲሆን ቀሪው 35 አክሲዮን በጋብቻ ውስጥ የተገዛ ነው፣ የአክሲዮኑ ውጤት የሆነው ሱቅና

ማስታወሻ፡ - ይህ የ ሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነ ድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገ ለግልም!

መጋዘን በጋብቻ ውል የጋራ እንዲሆን ሥምምነት ያደረግን በመሆኑ የአክሲዮኑና የሚገኘው ጥቅም የጋራ ንብረት ተብሎ እንዲወሰን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ባቀረቡት መልስ አክሲዮኑ ከጋብቻ በፊት የተገዛ ነው፣ ቀሪ ክፍያ ብር 93,000.00 በጋብቻ ውስጥ የተከፈለውን ግማሹን ለተጠሪ ለመክፈል ዝግጁ ነኝ፣ በሥምምነት የጋራ የተደረገ አክሲዮን የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክሮች እና የቀረቡ ማስረጃዎችን የመዘገበ ሲሆን በዚህም መሠረት የነባር አጠቃላይ ንግድ አክሲዮን የንግድ ማህበር በተላከ ማስረጃ ጠቅላላ ብር 268,000 (ሁለት መቶ ስልሳ ስምንት ሺህ) የአክሲዮን ክፍያ በአመልካች ከ 21/11/2000 ዓ.ም - 7/06/2007 ዓ.ም ድረስ መከፈሉን እንዲሁም እስካሁን ምንም አይነት የትርፍ ክፍፍል አለመደረጉን ፣ከዚህ ቀደምም ነባር አጠቃላይ የንግድ ስራ በቀን 17/6/2014 ዓ.ም በተፃፈ ውጤት አመልካች ጳጉሜ 2/2001 ዓ.ም አንድ የአክሲዮን ድርሻ የአንዱ ዋጋ ብር 7500 የገዙና ከአንድ አክሲዮን ወደ ሰላሳ ስድስት አክሲዮን በቀን 17/11/2010 ያደገ መሆኑን እንዲሁም ሱቆቹን ተከራይተው ያሉ መሆኑን ገልጿል፡፡ ፍርድ ቤቱ በሰጠው ውሳኔ ግራ ቀኝ በ15/07/2009 ዓ/ም ያደረጉትን ስምምነት በፍርድ ቤት የፀደቀ ሲሆን በዚሁ ስምምነትም በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 1 የቤት ቁጥር 64/ሀ የንግድ ቤታቸው የጋራ ሃብት ስለመሆኑ ስምምነት ያደረጉ በመሆኑ ተጋቢዎች ንብረትን በተመለከተ ያደረጉት ስምምነት በይዘት ደረጃ የቤት ቁጥር ጠቅሰው የተስማሙበት የንግድ ቤት መነሻው የአክሲዮን መብት ጋር የተያያዘ መሆኑን መረዳት የተቻለ ሲሆን ከንግድ ሱቆቹ ጋር በተያያዘ የአክሲዮን ክፍያዎቹ ክፍያ የተጀመረው ከጋብቻው በፊት በአመልካች ቢሆንም በትዳር ውስጥ ከጋራ ገቢያቸውና ጥረታቸው የከፈሉ ስለመሆኑ በማስረጃዎች የተረጋገጠ ስለሆነ የአክሲዮን ክፍያው መብት ያለው ሰው የፍሬውም ባለመብት ስለሚሆን የጋራ ንብረት ነው በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ይግባኙን በመመርመር ቅሬታ የቀረበበት ውሳኔ ስህተት ያለበት ሆኖ ስላልተገኘ ይግባኙን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

አመልካች ሐምሌ 20 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይህን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ሲሆን ይዘቱም፡- በፍቺ ወቅት ከጋብቻ በፊት የተፈሩ ንብረቶች የግል መሆናቸው በማስረዳት መልሶ መውሰድ እንደሚቻል በሕጉ በተደነገገው መሰረት አመልካች ክርክር የተነሳበትን ንብረት ከጋብቻ በፊት ስለመግዛቱ አስረድቼ እያለ የስር ፍርድ ቤቶች  የመጨረሻውን ክፍያ ብቻ በማየት ንብረቱ በሙሉ የጋራ ንብረት ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ የህግ መሰረት የሌለው ነው፣ እንደ አክሲዮን ግዥ በመሳሰሉት በየጊዜው በሚከፈል ክፍያዎች የሚደረጉ ውሎች መብት ተፈጠረ እና ባለቤትነት ተመሠረተ የሚባለው

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ውል ተፈጽሞ ክፍያ መከፈል ሲጀመር እንጂ የመጨረሻው ክፍያ ተጠናቆ በተከፈለበት ጊዜ አይደለም፣አመልካች አክሲዮን ለመግዛት ውል ያደረገው በ2001 ዓ.ም ጋብቻ ሳይፈጸም ማለትም ከጥር 25 ቀን 2006 ዓ.ም በፊት ሲሆን መከፈል ካለበት አጠቃላይ ብር 270,000 (ሁለት መቶ ሰባ ሺ ብር) ውስጥ 177,000 (አንድ መቶ ሰባ ሰባት ሺ ብር) ከጋብቻ በፊት አመልካች በራሴ መክፈሌን ፣ በጋብቻ ውስጥ በጋራ ደግሞ ብር 93,000 (ዘጠና ሶስት ሺ ብር) መከፈሉን ባልተስተባበለበት ሁኔታ ተጠሪ ከከፈሉት ላይ የሚገባቸውን ብር 46,500 ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤቶች በአጠቃላይ ላይ መወሰኑ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የሰበር ሰሚው ችሎትም የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ክርክር የቀረበበትን አክሲዮን አስመልክቶ የአሁን ተጠሪ ከጋብቻ በፊት የነበረው አንድ አክስዮን ብቻ ሆኖ በጋብቻ ውስጥ ተጨማሪ 35 አክሲዮን ተገዝቶ በጠቅላላው 36 አክሲዮን እንደደረሰ ገልጸው የጋራ ሊባል ይገባል በማለት ተከራክረዋል፣ አመልካች በበኩላቸው ሁሉም አክሲዮን የተፈረመው ከጋብቻ በፊት ሆኖ መከፈል ከሚገባው አክሲዮን እዳ ውስጥም አብዛኛው ከጋብቻ በፊት ተከፍሎ በጋብቻ ውስጥ ቀሪ ብር 93,000 ( ዘጠና ሶስት ሺህ ብር ) ብቻ መሆኑን ጠቅሰው ተጠሪ ይህንን ከሚካፈሉ በቀር አክሲዮኑ የጋራ ሊባል አይግባም በማለት ተከራክረዋል፣ ከዚህ የግራ ቀኙ ክርክር አኳያ አክሲዮኑ የጋራ ነው በሚል በስር ፍርድ ቤቶች የሰተጠው ውሳኔ ተገቢው ጭብጥ ተይዞ እና ለጉዳዩ አወሳሰን አስፈላጊ የሆነው ፍሬ ነገር ተጣርቶ ስለመሆኑ ግራ ቀኙ በተገኙበት ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባው በመሆኑ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ታዟል ፡፡

ተጠሪ ሰኔ 14 ቀን 2016 ዓ.ም የሰጡት መልስ ይዘት፡- በስር ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ አክስዮኑ የጋራ ነው በማለት ክስ ያቀረብኩት በተጠሪ እና አመልካች መካከል መጋቢት 15 ቀን 2009 ዓ.ም የተደረገ ስምምነት ፍርድ ቤት ቀርቦ በመ/ቁ 117401 መጋቢት 27 ቀን 2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት በተሰጠ ውሳኔ የጸደቀ ውልን መሰረት በማድረግ እና ከትዳር በፊት አመልካች የገዛው 1 አክሲዮን ሲሆን በትዳር ውስጥ ደግሞ 35 አክስዮን ጨምረን ገዝተናል ፣የአክሲዮኑን የመግባቱ ዋና ጥቅም የሆነውን ሱቅ እና መጋዘን ግንባታው ከ 2003 እስከ 2008 ዓ.ም ድረስ ተከናውኖ እስኪያልቅ በመጠበቅ በ2008 ዓ.ም በትዳር ውስጥ የተረከብን መሆኑን ፍርድ ቤቱ ለጉዳዩን ለመወሰን አግባብነት ያለው ጭብጥ ይዞ ግራቀኛችን ካቀረብናቸው ማስረጃችዎች በተጨማሪ በራሱ ትዕዛዝ ያቀረባቸውን ማስረጃዎች በመመርመር የሰጠው ውሳኔ፤ ወሳኔውን ለመስጠት የሚያስችሉ ፍሬ ነገሮችን ያጠራ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡ አመልካች በሰጡት የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡

የግራ ቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ህጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

እንደመረመርነው ጉዳዩ የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩን በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሰረት መምራት እና መቆጣጠር የፍርድ ቤቱ ኃላፊነት ሲሆን በተገቢው ሁኔታ ካልተመራ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ዓላማዎች የሆኑትን እንደ አንጻራዊ እውነትን የመፈለግ፣ ሥነ-ሥርዓታዊ ፍትህ፣ ክርክርን ውጤታማ፣ ወጭና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ መምራት የመሳሰሉትን ማሳካት ስለማይቻል የተከራካሪዎችን መብት ይነካል፡፡ ክርክር የሚወሰነው በተጠየቀው ዳኝነት አግባብ እንደሆነ የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 182(2) ላይ ተመልክቷል፡፡ ፍርድ ቤቱም ከቀረበው ዳኝነት አኳያ ከግራቀኙ ክርክር በመነሳት በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 246 እና ተከታዮቹ መሠረት በተነሱት ጉዳዮች ጭብጥ መስርቶ ውሳኔ የመስጠት ኃላፊነት አለበት፡፡ በክርክር አመራር ሥርዓት ሂደቱ የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍል እና የሀብት ማጣራት ስራ ሲከናወን በቤተሰብ ሕጉ ከፍቺ በኂላ ሀብት ስለሚጣራበት ሁኔታ የተዘረጋውን ሥርዓት ግምት ውስጥ ማስገባት ይገባል፡፡

ጋብቻ በፍቺ ከፈረሰ በኂላ ተጋቢዎች የነበሩት በንብረት ክፍፍል ሂደት ሊጣራላቸውን የሚገባውን የንብረት ዝርዝር ማቅረብ ያለባቸው ስለመሆኑ በፌዴራል የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 85 እና ተከታይ ድንጋጌዎች አቀራረጽ ይዘት የምንገነዘበው ነው፡፡ ተጠሪም በዚሁ አግባብ በነባር አጠቃላይ ንግድ አክሲዮን ማሕበር በአመልካች ሥም ከጋብቻ በፊት የነበረው አንድ አክሲዮን ሲሆን ቀሪው 35 አክሲዮን በጋብቻ ውስጥ የተገዛ ነው፣ የአክሲዮኑ ውጤት የሆነው ሱቅና መጋዘን በጋብቻ ውል የጋራ እንዲሆን ሥምምነት ያደረግን በመሆኑ የአክሲዮኑና የሚገኘው ጥቅም የጋራ ንብረት ተብሎ እንዲወሰን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ባቀረቡት መልስ አክሲዮኑ ከጋብቻ በፊት የተገዛ ነው፣ ቀሪ ክፍያ ብር 93,000.00 በጋብቻ ውስጥ የተከፈለውን ግማሹን ለተጠሪ ለመክፈል ዝግጁ ነኝ፣ በሥምምነት የጋራ የተደረገ አክሲዮን የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ከአክሲዮኑ መብት ውጤት የሆነ የንግድ ቤት ላይ  የጋራ ሀብት እንዲሆን ግራቀኙ መስማማታቸው በመግለጽና የአክሲዮን ክፍያው ሙሉ በሙሉ ከጋብቻ በፊት ተከፍሎ ያልተጠናቀቀና ክፍያም ከጋብቻ በኂላ መከፈሉን በምክንያትነት በማስፈር 36 አክሲዮኖች የግራቀኙ የጋራ ንብረት ስለሆኑ እኩል ይካፈሉ በማለት ወስኗል፡፡

በፔዴራል የተሻሻለው የቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 57 መሠረት ከጋብቻ በፊት የተፈራ ንብረት የግል ንብረት ነው፣ የጋራንብረት ሊሆን የሚችለው በጋብቻ ውል ንብረቱ የጋራ እንዲሆን ሥምምነት ከተደረገበት ነው፤ አክሲዮኑ የተገዛው ከጋብቻ በፊት ንብረቱ የአመልካች የግል ሀብት ሆኖ የሚቀጥል ነው፣ የአክሲዮኑ ቀሪ ዋጋ በጋብቻ ውስጥ መከፈሉ ንብረቱን የጋራ አያደርገውም፣ ክፍያው በግል ሀብት ላይ የጋራ ገንዘብ መቀላቀሉን ነው የሚያሳየው፣ እንዲሆነ በሆነ ጊዜ ከግል ሀብት ጋር የተቀላቀለውን ገንዘብ በመለየት የጋራ ገንዘቡን ብቻ እንዲካፈሉ ሊወሰን ይገባል፡፡ በሌላ በኩል የተጠሪ የክስ ዳኝነት የሚያሳየው ከጋብቻ በፊት የተገዛው አንድ አክሲዮን ሲሆን ከጋብቻ በኂላ ተጨማሪ 35 አክሲዮን በጋራ ገዝተናል የሚል ነው፤ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ አክሲዮን ማሕበሩ የአመልካች አክሲዮን መጠን ከአንድ ወደ 36 በ2010 ዓ/ም ያደገ ስለመሆኑ ማስረጃ መቅረቡን መዝግቧል፡፡ ነገር ግን ፍርድ ቤቱ ጋብቻ ከፈጸሙ በኂላ ተጨማሪ 35

አክሲዮን የገዙ መሆን አለመሆኑን፣ የአክሲዮን መጠኑ ማደግ አለማደጉን በጭብጥነት ባለመያዙ በጉዳዩ ላይ አከራክሮ ውሳኔ አልሰጠበትም፡፡ ፍርድ ቤቱ የአክሲዮን መብት ውጤት የሆነ የንግድ ቤት በሥምምነት የጋራ ያደረጉት መሆኑን በውሳኔው የገለጸ ቢሆንም ጋብቻው በ2006 ዓ/ም ከተፈጸመ እና ሥምምነቱ የተደረገው በ2009 ዓ/ም መሆኑና በፍርድ ቤት መጽደቁ መገለጹ ሲታይሥምምነቱ ጋብቻ ሲፈጸሙ የተደረገ የጋብቻ ውል ነው ወይስ አይደለም፣ በጋብቻ ግንኙነት መካከል የተደረገ ውል ከሆነ ሕጋዊ ውጤቱ ምንድን ነው፣ ግራቀኙ ያላቸውን አለመግባባት ለመፍታት ያደረጉት የእርቅ ሥምምነት ከሆነና ስለንግድ ቤቱ የተደረገው የሥምምነት አካል ቀደም ሲል ክርክሩን ሲመለከት የነበረው ፍርድ ቤት ያልተቀበለው ከሆነ ሕጋዊ ውጤቱ ምንድን ነው የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ የተከራካሪዎችን የመደመጥ መብት በማክበር ውሳኔ አለመስጠቱ ሆነ ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ ይሕንን ሳያርም ማለፉ መሠረታዊ የሆነ የክርክር አመራር ግድፈት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 303744 ግንቦት 24 ቀን 2015 ዓ/ም እና የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 171490 መጋቢት 18 ቀን 2015 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1)(ለ) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በውሳኔ የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ ግራቀኙ ጋብቻ ከፈጸሙ በኋላ በነባር አጠቃላይ ንግድ አ/ማ ተጨማሪ 35 አክሲዮን የገዙ መሆን አለመሆኑን፣ የአክሲዮን መጠኑ ማደግ አለማደጉን፣ የአክሲዮን መብት ውጤት የሆነ የንግድ ቤት በሥምምነት የጋራ የተደረገው ጋብቻ ሲፈጸሙ የተደረገ የጋብቻ ውል ነው ወይስ አይደለም፣ በጋብቻ ግንኙነት መካከል የተደረገ ውል ከሆነ ሕጋዊ ውጤቱ ምንድን ነው፣ ግራቀኙ ያላቸውን አለመግባባት ለመፍታት ያደረጉት የእርቅ ሥምምነት ከሆነና ስለንግድ ቤቱ የተደረገው የሥምምነት አካል ቀደም ሲል ክርክሩን ሲመለከት የነበረው ፍርድ ቤት ያልተቀበለው ከሆነ ሕጋዊ ውጤቱ ምንድን ነው የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ ክርክራቸውንና ማስረጃቸውን በመስማት በሕግ መሠረት እንዲወሰን በሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(2) መሰረት ጉዳዩን መልሠናል፡፡

3. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ፍርድ ቤት በውሳኔው መሠረት እንዲፈጽም አዘናል፡፡ ይጻፍ
- አፈጻጸሙ ላይ የተሰጠው እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አ፤በት

ብ/ም

የሰ.መ.ቁ 251213
ጥቅምት 07 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

ሐብታሙ እርቅይሁን

አመልካቾች፡- 1. ወ/ሮ ጥሩወርቅ ተስፋ
2. ወ/ሮ ደብሪ ተስፋ
3. አቶ አበበ ተስፋ
4. አቶ ጥበበ ተስፋ
5. ወ/ሮ ቆንጂት ተስፋ

ጠበቃ አበባ መንግስቱ ቀርቧል

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ተዋበች ተስፋ - አልቀረቡም

መዝገቡ ለፍርድ የተቀጠረ ነው፡፡ በዚሁ አግባብ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካቾች ሐምሌ 21 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 207000 የካቲት 17 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 306395 ሐምሌ 05

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ብይን መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ ውርስን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌደራል መጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካቾች እና አቶ ሰለሞን ተስፋ የተባሉ ግለሰብ ከሳሾች፤ የሕጻን እንዳልካቸው ተስፋና የሕጻን አማዲ ተስፋ ሞግዚት ወ/ሮ መነን ዳንኤል፤ ወ/ት ዮርዳኖስ አርካካ፤ የአሁን ተጠሪ እና ወ/ሮ መሰረት ተስፋ ደግሞ ጣልቃ ገቦች በመሆን የተከራከሩ ሲሆን በመዝገቡ ተከሳሽ አልነበረም፡፡

አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- ወላጅ እናታችን ወ/ሮ አለሚቱ ንጉሴ ሕዳር 27 ቀን 2014 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፤ አመልካቾችም ወራሽነታችንን አረጋግጠናል፤ ስለሆነም ሟች በሕይወት እያሉ ያፈሩት የውርስ ሐብት ይጣራልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት የውርስ ሐብቱ ተጣርቶ እንዲቀርብ በሰጠው ትእዛዝ መሰረት በቀን 02/13/2014 ዓ.ም የተጻፈ የውርስ አጣሪ ሪፖርት ቀርቧል፡፡ ፍርድ ቤቱ በመቀጠል በቀረበው የውርስ ሪፖርት ላይ ግራ ቀኙ አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ካደረገ በኋላ መርምሮ በፍ/ብ/ሕ/ቁ ቁ 896 እና 897 (1 ) እና (2) የኑዛዜው ተጠቃሚ ነኝ የሚል ሰው ኑዛዜውን ለማረጋገጥ የሚችለው የኑዛዜውን ዋና ፅሁፍ በማቅረብ ወይም ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው ሰው ወይም በፍርድ መዝገብ ቤት ሹም ትክክለኛ ሆኖ የተመሰከረለት ግልባጭ በማቅረብ ካልሆነ በቀር በሌላ መንገድ ለማስረዳት እንደማይቻል ተመልክቷል፤ የስር 1ኛ እና 2ኛ ጣልቃ ገቦች የኑዛዜውን ዋና ያላቀርቡ ሲሆን የቀረበውን የኑዛዜ ገፅ ለገፅ ፎቶ ትክክለኛነቱ በተገቢው አካል ቀርቦ የተመሰከረ አይደለም፤ በተያያዘም በምስክር እናስረዳለን በማለት ያቀረቡትን መከራከሪያ በተመለከተ ኑዛዜውን ዋና ወይም የተረጋገጠ ገልባጭ ማቅረብ ሳያስፈልግ በሌላ አይነት ማስረጃ ኑዛዜን ለማስረዳት የሚቻለው በጥፋት ወይም በቸልተኝነት ነዛዜውን እንዲጠፋ ካደረገው ሰው የጉዳት ኪሳራን ለማግኘት ብቻ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ 897(3) ተመልክቷል፤ ይህ ዓይነት ክርክር ባልተነሳበት ሁኔታ በምስክር እናስረዳለን በማለት ያቀረቡትን ክርክር ፍርድ ቤቱ አልተቀበለውም፤ ስለሆነም የስር 1ኛ እና 2ኛ ጣልቃ ገቦች ኑዛዜ አለ በማለት ያቀረቡት መከራከሪያ የሕግ መሰረት የሌለው በመሆኑ በዚህ ረገድ በውርስ አጣሪው ሪፖርት ላይ የተገለጸው የሚነቀፍ አይደለም፤ ሌላው ጥቅምት 17 ቀን 1992 ዓ.ም የተደረገው የስጦታ ውል ተጠሪ በተስፋ ገ/ሥላሴ ዘብሔረ ቡልጋ ኃ/የተ/የግ/ማህበር በውርስ ሊገኝ የሚችል የአክሲዮን ድርሻ እንዳያገኙ የሚከለከል ይዘት የሌለው በመሆኑ እና ከወራሾች በኩል የቀረበ ክርክር የሌለ በመሆኑ በዚህ ጉዳይ ላይ የውርስ አጣሪ የደረሱበት መደምደሚያ አግባብ አይደለም፤ ስለሆነም በተስፋ ዝሥላሴ ዘብሔረ ቡልጋ ኃላ/የተ/የግ/ማሕበር በሟች ስም የሚገኝ 4,400 ( አራት ሺህ አራት መቶ ) አክሲዮን የስር ከ1-6ኛ ያሉ አመልካቾች፤ የሟች አቶ እንዳልካቸው ተስፋ ወራሾች በጋራ ( የስር 1ኛ እና

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

2ኛ ጣልቃቦች)፤ ተጠሪ እና የስር 4ኛ ጣገብ እያንዳንዳቸው 1/9 ኛ ድርሻ አላቸው በማለት የውርስ አጣሪው ያቀረቡትን ሪፖርት በማሻሻል ዉሳኔ ሰጥቷል፤ ለዚህ ሰበር ምክንያት ባልሆኑ ሌሎች ጉዳዮች ላይም ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ አስተላልፏል፡፡

አመልካቾች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት ይግባኛቸው ተሰርዟል፡፡

አመልካቾች ሐምሌ 21 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይህን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ሲሆን ይዘቱም፦ ሟች ቀኛዝማች ተስፋ ገ/ስላሴ እና ወ/ሮ አለሚቱ ንጉሴ ተስፋ ገ/ሥላሴ ዘብሔረ ቡልጋ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማሕበርን ሊያቋቁሙ ሲሉ ተጠሪ ማሕበሩን በተመለከተ ወደፊትም ቢሆን ምንም አልፈልግም ለእኔ ንብረት ስጡኝ በማለታቸው ጥቅምት 17 ቀን 1992 ዓ.ም በተጻፈ የስጦታ ውል ማሕበሩ እንደማይመለከታቸው በመጥቀስ ቤት እና ገንዘብ ከሰጧቸው በኋላ ሟቾች ብቻቸውን ማሕበሩን አቋቁመዋል፤ አመልካቾች ይህንኑ በመግለጽ ተጠሪ ማህበሩ እንደማይመለከታቸው አስረድተናል፤ የአመልካቾች እና የተጠሪ ወላጅ እናት ሟች ወ/ሮ አለሚቱ ንጉሴ ጋር በአንድ የስጦታ ውል የሰጡት የሟች አባታቸው ድርሻን ከስጦታው በመነሳት እንዳይወርሱ የተደረገ በመሆኑ እንዲሁም ሌሎች ለውርስ አጣሪው የቀረቡ ሼሩን ሊወርሱ እንደማይገባ የሚያረጋግጡ በርካታ ማስረጃዎች አሉ፤ ተጠሪ በውርስ ማጣራቱ ልካተት የሚል አቤቱታ ሲያቀርቡ አመልካቾች ተጠሪ በማህበሩ ውስጥ ድርሻ እንደሌላቸው የሚያስረዱ ማስረጃዎችን በማቅረብ ተከራክረናል፤ ፍርድ ቤቱ አመልካቾች አልተቃወሙም በማለት የውርስ አጣሪውን ሪፖርት በማሻሻል የሰጠው ውሳኔ ተገቢነት የለውም፤ የውርስ አጣሪው ተጠሪ በማህበሩ ውስጥ ድርሻ እንዳይኖራቸው በስጦታ የታገዱ በመሆኑ ከማሕበሩ ላይ ድርሻ የላቸውም በማለት ያቀረበው የውርስ ሪፖርት ሕግን መሰረት ያደረገ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ይህንን በማሻሻል የሰጠው ውሳኔ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የስር ፍርድ ቤት የሟች ወ/ሮ አለሚቱ ንጉሴ ድርሻ የሆነው የተስፋ ገ/ስላሴ ዘብሄረ ቡልጋ ኃ/የተ/የግ/ማ አክሲዮን የውርስ ሀብት ድርሻን በተመለከተ ተጠሪ 1/9ኛ ድርሻ አላቸው በማለት የወሰነው አመልካቾችና ተጠሪ ለውርስ አጣሪ ሪፖርቱ በሰጡት አስተያየት ላይ ግራ ቀኙ በአግባቡ እንዲከራከሩ አድርጎ ነውን? የሚለውን ነጥብ ለመመርመር ሲባል ተጠሪ ቀርበው መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪ ሰኔ 06 ቀን 2016 ዓ.ም የሰጡት መልስ ይዘት በአጭሩ፦ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የተሰጠው የግራቀኛችን የሰው እና የሰነድ ማስረጃ ቀርቦ በቂ ክርክር ከተደረገበት በኋላ ነው፤ ተጠሪ በማሕበር መስራችነቴ ያቀረብኩት የድርሻ ጥያቄ የለም፤ የማሕበሩ መስራች የሆኑት እናቴ ወ/ሮ አለሚቱ ተጠሪን ከውርስ ውጪ የሚያደርግ ኑዛዜ አልተዉም፤ እናቴ በማሕበሩ ካላቸው የውርስ ድርሻ ላይ በውርስ ማግኘት

የለብኝም የሚል ማረጋገጫ አልቀረበም፤ ሟች እናቴ ኑዛዜ አልተዉም፤ በማሕበሩ ውስጥ የሼር ድርሻ እንዳይኖረኝ አልታገድኩም፤ የስጦታ ውሉ መስራች ለመሆን ፍላጎት የሌለኝ መሆኑን የሚያስረዳ እንጂ ሟች ከሞቱ በኋላ የሚሰጠውን የውርስ ሐብት ድርሻ የሚመለከት አይደለም፤ የውርስ አጣሪው ባቀረበው ሪፖርት ላይ ግራ ቀኛችን አስተያየት እንድንሰጥ ከተደረገ በኋላ ፍርድ ቤቱ የቀረቡ ማረጃዎችን በመመልከት ሪፖርቱን አሻሽሏል፤ አመልካቾች ተደረገ የሚሉት የስጦታ ውል ተጠሪን ጨምሮ ለ7 ሰዎች የተደረገ ከመሆኑም በላይ ተጠሪ የማህበሩ አባል መሆን አልፈልግም ማለታቸውን ከመግለጽ ውጪ ሟች አለሚቱ ንጉሴ ሲሞቱ ከአክሲዮን ድርሻ ላይ አልወርስም የሚል ባመሆኑ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ማስረጃን በመመዘን የተሰጠ ተገቢ ወሳኔ ነው፤ አመልካቾች ያቀረቡት የሟች ቀኝ አዝማች ተስፋ ገ/ሥላሴ ኑዛዜ የሚስታቸው ሟች አለሚቱ ንጉሴን ፍላጎት የሚያስረዳ ባለመሆኑ ለጉዳዩ ተገቢነት ያለው ማስረጃ አይደለም፤ ተጠሪ ያቀረብኩት ጥያቄ ከማህበሩ የድርሻ ጥያቄ ሳይሆን የማህበሩ መስራች ከሆኑት ሟች እናቴ ወ/ሮ አለሚቱ ንጉሴን ድርሻ በውርስ የማገኘው ድርሻ አልፈልግም በማለት የቀረበ አይደለም፤ አመልካቾች ሟች እናታችን ኑዛዜ ያልተዉ መሆናቸውን እያወቁ ሟች አባታችን ያደረጉትን ኑዛዜ በማቅረብ ተጠሪ የሟች እናታችንን የውርስ ሀብት መውረስ አትችልም በማለት ያቀረቡት ክርክር የሕግ መሰረት የለውም፤ ስለሆነም ውሳኔው ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን ይመስላል፡፡ ይህ ችሎትም ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ምክንያት ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

አመልካቾች ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የሟች ወ/ሮ አለሚቱ ንጉሴ ድርሻ የሆነው የተስፋ ገ/ስላሴ ዘብሄረ ቡልጋ ኃ/የተ/የግ/ማ አክሲዮን የውርስ ሀብት ድርሻን በተመለከተ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ነው በማለት በዋነኝነት የሚከራከሩት ተጠሪ በውርስ ማጣራቱ ልካተት የሚል አቤቱታ ሲያቀርቡ አመልካቾች ተጠሪ በማህበሩ ውስጥ ድርሻ እንደሌላቸው የሚያስረዱ ማስረጃዎችን በማቅረብ በተከራከርነው መሰረተ ውርስ አጣሪው ተጠሪ በማህበሩ ላይ ድርሻ የላቸውም በማለት በአግባቡ የሰጠውን አስተያየት ፍርድ ቤቱ አመልካቾች አልተቃወሙም በማለት የውርስ አጣሪውን ሪፖርት በማሻሻል የሰጠው ውሳኔ ተገቢነት የለውም በሚል ነው፡፡ በአንጻሩ ተጠሪ አመልካቾች ተደረገ የሚሉት የስጦታ ውል ተጠሪን ጨምሮ ለ7 ሰዎች የተደረገ ከመሆኑም በላይ ተጠሪ የማህበሩ አባል መሆን አልፈልግም ማለታቸውን ከመግለጽ ውጪ ሟች አለሚቱ ንጉሴ ሲሞቱ ከአክሲዮን ድርሻ ላይ አልወርስም የሚል አይደለም፤ አመልካቾች ያቀረቡት የሟች ቀኝ አዝማች ተስፋ ገ/ሥላሴ ኑዛዜ የሚስታቸው ሟች አለሚቱ ንጉሴን ፍላጎት የሚያስረዳ ባለመሆኑ ለጉዳዩ ተገቢነት ያለው ማስረጃ አይደለም፤ ተጠሪ ያቀረብኩት ጥያቄ ከማህበሩ የድርሻ ጥያቄ ሳይሆን የማህበሩ መስራች ከሆኑት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ሟች እናቴ ወ/ሮ አለሚቱ ንጉሴን ድርሻ በውርስ የማገኘው ድርሻ አልፈልግም በማለት የቀረበ አይደለም በሚል ይከራከራሉ፡፡

ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ እንደቻልነው ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ግራቀኙ በውርስ አጣሪው ሪፖርት ላይ አስያየት እንዲሰጡ በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት አመልካቾች ሪፖርቱ ሕጉን ተከትሎ የተሰራ በመሆኑ እንዲፀድቅልን በማለት አስተያየት እንደሰጡ፤ የስር 1ኛ እና 2ኛ ጣልቃ ገቦች በሰጡት አስተያየት የውርስ አጣሪው ባቀረብንላቸው ኑዛዜ ኮፒ መነሻነት ኑዛዜውን ማፈላለግ ሲገባቸው ሰነዱን በመተቸት አልቀበልም ማለታቸው ተገቢ እንዳልሆነ፤ ኑዛዜውን ለማግኘት ተገቢው ጥረት ሊደረግ እንደሚገባ፤ በውርስ ሐብት ዝርዝር ላይ የተስፋ ገብረስላሴ ዘብሔረ ቡልጋ አክሲዮን ማሕበር ሲያስተዳድረው የነበረው ሰፊ ይዞታ ለልማት እና ቅርስ በማለት ሲወስድ የተሰጠ ምትክ ቦታ እና ካሳ እንዲጣራላቸው ጠይቀው በሪፖርቱ ላይ የለም በሚል እንደተገለጸ፤ 2515.3 ካ.ሜ ስፋት ያለው ቦታና ቤት ከሟች ተወስዶ ለቅርስነት የተመዘገበ መሆኑ ተገልጾ እያለ ምትክ ቦታና ቤት አልተሰጠም ካሳ አልተከፈለም መባሉ ተገቢ እንዳልሆነ፤ ምትክ ካሳ እና ጥያቄ ክትትል ሳይደረግበት እልባት ሳያገኝ ቀርቶ ከሆነ ስለመኖሩ ወይም የተጀመረ ተግባር ካለ የሚመለከተው አካል ማረጋገጫ እንዲሰጥ፤ ጥያቄው ቀርቦ የማያውቅ ከሆነም የውርስ ሐብት ሆኖ በወራሾች መካከል ክፍፍል እንዲደረግ፤ በአክሲዮን ማሕበሩ ያለው ሀብት እና ድርሻ እንዲታወቅ ጥያቄ አቅርብን የነበረ ሲሆን የውርስ አጣሪ ሳይቀበሉት የቀረ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ በገለልተኛ ሒሳብ አጣሪ የድርጅቱ ሒሳብ ተጣርቶ ታውቆ ድርሻ እንዲለይ በማለት አስተያየት የሰጡ መሆኑን፤ **የአሁን ተጠሪ በሰጡት አስተያየት** ደግሞ የሟች ተስፋ ገ/ሥላሴ እና የወ/ሮ አለሚቱ ንጉሴ ልጅ እና የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ በመሆኔ ከእህት እና ወንድሞቻቸው ጋር እኩል መብት እንዳላቸው፤ በተስፋ ገ/ሥላሴ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማሕበር ውስጥ የብር 400000 የአክሲዮን ድርሻ ውስጂ የማሕበሩ አባል እንዲሆን ተጠይቀው ፈቃደኛ ባለመሆናቸው በምትኩ ሲጠቀሙበት የነበረውን በወቅቱ እኩል ዋጋ የነበረውን እና ተመጣጣኝነት ያለውን ቤ.ቁ 045 እንዲወስዱ በቀን 17/02/1992 ዓ.ም የተፈጠረ ሰነድ በተወላጆች መካከል መበላለጥ እንዳይፈጠር ለማድረግ እንደሆነ፤ ይህ መደረጉ ከወላጆቻቸው እልፈት በኂላ የውርስ ድርሻ ጥያቄ እንዳያቀርቡ እንደማይከለክላቸው በመግለጽ አስተያየት እንደሰጡ ነው፡፡

በመሠረቱ ውርስ ማጣራት ማለት የውርሱ ተቀባይ እነማን እንደሆኑ እና የውርስ ሀብቱ ምን እንደሆነ መወሰን፣ ለውርሱ የሚከፈሉትን ክፍያዎችን መቀበል እና ለመክፈል አስገዳጅ የሆኑ የሟች እዳዎችን መክፈል እንዲሁም ሟቹ በኑዛዜ ስጦታ ላደረገላቸው ሰዎች የሰጣቸውን ስጦታ መክፈል ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ህ/ቁጥር 944 ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚሁ ወሰን ውስጥ የውርስ አጣሪ ስራ እና የስልጣን ወሰኑ እስከ ምን ድረስ እንደሆነ በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 956 እና 957 ስር ተመልክቷል፡፡ የውርስ አጣሪ ተደርጎ የተሾመው ሰውም የማጣራት ስራውን ሲጨርስ ወራሾች ለሆኑት እና የማጣራት ስራውን ሲመራ ለነበረው ፍርድ ቤት በተቀመጠው የጊዜ ገድብ ውስጥ የስራ ክንውን ጉዳዩን የሚያመላክት ሪፖርት ማቅረብ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

እንደሚገባው በቁጥር 960 ስር ተመልክቷል፡፡ በሪፖርቱ መካተት ከሚገባቸው ጉዳዮች ውስጥ አንዱ በውርስ ማጣራት ሂደቱ ውስጥ የውርስ ሀብት ነው የተባለውን ንብረት አስምልክቶ አልያም ከማጣራት ተግባሩ ጋር ተያይዞ በተከራካሪ ወገኖች የተነሳውን ክርክር ከተገቢ ማስረጃ ጋር አጠናቅሮ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ እንዲሰጥበት ማቅረብ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ህግ ቁጥር 956 ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህ መልኩ ሪፖርት የቀረበለት ፍርድ ቤትም ሪፖርቱን ከማፅደቁ በፊት ተከራካሪ ወገኖች ስለአጣሪው ሪፖርት ይዘት በአጠቃላይ፤ በተለይ ደግሞ አከራካሪ በሆኑት ነጥቦች ላይ ያላቸውን ክርክር ሰምቶ እና ማስረጃዎቹን መዝኖ ተገቢውን ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባል፡፡ የውርስ አጣሪ ሪፖርቱ ለተከራካሪ ወገኖች እንዲደርስ የተፈለገበት አንዱ ምክንያትም የዚህኑ ዓይነት የመከራከር እድል ለመፍጠር እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በሰ.መ.ቁ 231692 በሰጠው ውሳኔ በዚህ ረገድ በየትኛውም እርከን ላይ ለሚገኙ ፍርድ ቤቶች አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

በያዝነው ጉዳይ የውርስ ክርክሩን የመራው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የውርስ ሪፖርቱ ከቀረበለ በኋላ በውርስ አጣሪው ሪፖርት ላይ ግራቀኙ አስተያየት እንዲሰጡ ዕድል ሰጥቷል፡፡ በመቀጠልም አመልካቾች የውርስ አጣሪውን ሪፖርት አልተቃወሙ በሚል የተጠሪን አስተያየት መሠረት በማድረግ ጭብጥ መሠረት በማድረግ ጭብጥ ይዞ ወስኗል፡፡ ሆኖም የውርስ ማጣራት ሒደት በባሕርይው መደበኛ ስርአትን ስለማይከተል አዲስ ነገር በተፈጠረ ጊዜ የዜጎች የመደመጥ መብት ሊከበር ይገባ ነበር፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ካቀረበችው ክርክር አንጻር ክርክሯ ለአመልካቾች ደርሶ መልስ እንዲሰጡበት ከተደረገ በኋላ በጉዳዩ ላይ ጭብጥ ተይዞ ሊወሰን ይገባ ነበር፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በዚህ አግባብ አይቶ መወሰን ሲገባው ይህን ሳያደርግ ውሳኔ መስጠቱ፤ ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንን ሳያርም መቅረቱ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በውርስ አጣሪው ሪፖርት ላይ የሟች ወ/ሮ አለሚቱ ንጉሴ ድርሻ የሆነው የተስፋ ገ/ስላሴ ዘብሄረ ቡልጋ ኃ/የተ/የግ/ማ አክሲዮን የውርስ ሀብት ድርሻን በተመለከተ ተጠሪ ያቀረቡትን አዲስ የክርክር ሀሳብ ለአመልካቾች እንዲደርስ በማድረግ አስተያየታቸውን እንዲያቀርቡ በማድረግ እና ግራቀኙን በማከራከር ተገቢ ነው የሚለውን ትዕዛዝ በመስጠት አጣርቶ ቀደም ሲል በመዝገቡ ከተሰሙ ማስረጃዎች ጋር አገናዝቦ ውሳኔ እንዲሰጥበት ማድረግ ፍትሐዊ እና ሥነ ሥርዓታዊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 207000 የካቲት 17 ቀን 2015 ዓ.ም በተስፋ ዝሥላሴ ዘብሔረ ቡልጋ ኃላ/የተ/የግ/ማሕበር በሟች ስም የሚገኝ 4,400 ( አራት ሺህ አራት መቶ ) አክሲዮን የስር ከ1-6ኛ ያሉ አመልካቾች፤ የሟች አቶ እንዳልካቸው ተስፋ ወራሾች በጋራ ( የስር 1ኛ እና 2ኛ ጣልቃቦች)፤ ተጠሪ እና የስር 4ኛ ጣገብ እያንዳንዳቸው 1/9 ኛ ድርሻ አላቸው በማለት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የውርስ አጣሪው ያቀረቡትን ሪፖርት በማሻሻል ዉሳኔ የሰጠው የውሳኔ ክፍል፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 306395 ሐምሌ 05 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ብይን በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 መሠረት ተሻሽሏል፡፡ ከዚህ ውጪ ያለው የውሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡

2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በውሳኔ የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው መንገድ በውርስ አጣሪው ሪፖርት ላይ የሟች ወ/ሮ አለሚቱ ንጉሴ ድርሻ የሆነው የተስፋ ገ/ስላሴ ዘብሄረ ቡልጋ ኃ/የተ/የግ/ማ አክሲዮን የውርስ ሀብት ድርሻን በተመለከተ ተጠሪ ያቀረቡትን አዲስ የክርክር ሀሳብ ለአመልካቾች እንዲደርስ በማድረግ አስተያየታቸውን እንዲያቀርቡ በማድረግ እና ግራቀኙን በማከራከር ተገቢ ነው የሚለውን ትዕዛዝ በመስጠት አጣርቶ ቀደም ሲል በመዝገቡ ከተሰሙ ማስረጃዎች ጋር አገናዝቦ ተገቢ ያለውን ሕጋዊ ውሳኔ እንዲሰጥበት በማለት በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(2) መሠረት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻቻሉ፡፡
    - መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

መ/ዐ                    የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
## የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ. 251218

ቀን ፡- ጥቅምት 07 ቀን 2017 ዓ/ም

ዳኞች- እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካቾች፡-1. ዶ/ር ክንዴ ካሰኝና ቤተሰቦቹ ሕንጻ ሥራ ተቋራጭ ኃ/የተ/የግ/ማሕበር

2. ወ/ሮ አለሚቱ ገመቹ
3. ዶ/ር ሳሙኤል ክንዴ
4. ወ/ሮ እጸገነት ክንዴ

} ጠበቃ ታምራት ታለ ጌታ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ሀበሻ ኮንስትራክሽን ማቴርያል ልማት አ/ማ ነ/ፈጅ ሀረገወይን ዓለማየሁ ቀረቡ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍርድ**

ጉዳዩ የማሕበር ይፍረስልኝ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌደራል የመጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት በተደረገ ክርክር ተጠሪ ከሳሽ፤ 1ኛ አመልካች ተከሳሽ፣ 2ኛ-4ኛ ያሉት አመልካቾች ደግሞ ጣልቃ ገብ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ይዘት 1ኛ አመልካች የሆነው ዶ/ር ክንዴ ካሰኝ እና ቤተሰቦቹ ሕንጻ ሥራ ተቋራጭ ኃ/የተ/የግል ማሕበር እንዲፈርስ የጠየቀው ከማሕበሩ ጋር ነሀሴ 22 ቀን 2005 ዓ/ም የተደረገ የንብረት አስተዳደርና የሪል እስቴት ልማት ማኔጅመንት ውል ማድረጉንና የ1ኛ አመልካች ማሕበር ሥራ-አስኪያጅና ከፍተኛ የአክሲዮን ባለድርሻ የነበሩት ዶ/ር ክንዴ ካሰኝ ከሞቱ ጀምሮ ማሕበሩን የሚያስተዳድር አመራር መሰየም አልቻሉም፣ በዚህም ምክንያት በቂርቆስ ክፍለከተማ ወረዳ 7 በሚገኘው ይዞታው ላይ የተጀመረውን ግንባታ ለማጠናቀቅና ተጠሪ ለሦስተኛ ወገኖች የገባውን የውል ግዴታ ለመወጣት አልተቻለም፣ ፕሮጀክቱ በመቆሙ ምክንያት ተጠያቂነት እየመጣብኝ ነው፣ ከፕሮጀክቱ ላገኘው የሚገባኝን ጥቅም አጥቻለሁ፣ በንግድ ሕጉ መሠረት ማሕበሩ የተቋቋመበትን ዓላማ መፈጸም ካልቻለ ወይም አስፈላጊ የሆነ የአስተዳደር አካል ከሌለው በገንዘብ ጠያቂ በሚቀርብ ጥያቄ ሊፈርስ ይችላል፡፡ ስለሆነም 1ኛ አመልካች ማሕበር እንዲፈርስ እንዲወሰን ዳኝነት ጠይቋል፡፡ 1ኛ አመልካች ጉዳዩ በስር ፍርድ ቤት በሌለበት የታየ ሲሆን የአክሲዮን ድርሻ ያላቸው ከ2ኛ-4ኛ የተመለከቱት አመልካቾች በክርክሩ ጣልቃ በመግባት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ ከ1ኛ አመልካች ማሕበር ጋር ካደረገው ውል ጋር በተያያዘ ላጋጠመው ችግር በውሉ መሠረት መፍትሄ መፈለግ ሲገባቸው ማህበሩ እንዲፈርስ መጠየቅ የለበትም ከማለት በቀር ማህበሩ በሞት በተጓደሉ አባሉ ምትክ ሌሎች ባለ አክሲዮኖችን በማስገባትም ሆነ በሌላ አግባብ ህልውና እንዲኖረው የተደረገ ስለመሆኑ ወይም የአስተዳደር አካል የተሰየመለት ስለመሆኑ ያቀረቡት ክርክርም ሆነ ማስረጃ የለም፣ የ1ኛ አመልካች ማህበር ባለ አክሲዮን ወራሾች በፍርድ ቤት በክርክር ላይ በመሆናቸው ምክንያት ማህበሩ ህልውና እንዲኖረው የተደረገ ጥረት የሌለ መሆኑን፣ የአስተዳደር አካልም ያልተሰየመ መሆኑን በማመን የተከራከሩ በመሆኑ ይህ ደግሞ የሶስተኛ ወገኖችን ጥቅም የሚጎዳ በመሆኑ፣ ማህበሩም እንደ ማህበር ህልውና ኖሮት መስራት በማይችልበት ደረጃ ላይ የሚገኝ ከሆነ የንግድ ማህበሩ የሚቀጥልበት ምክንያት የሌለ በመሆኑ ማህበሩ እንዲፈርስ ሊያስወስን የሚያስችል በቂ ምክንያት ተደርጐ ሊወሰድ የሚችልነው፡፡ ተጠሪ ከ1ኛ አመልካች ጋር በገባው ውል መሠረት 57% ትርፍ ማግኘት የሚገባው የነበረ በመሆኑ ገንዘብ ጠያቂ መሆኑን ያሳያል፣ 1ኛ አመልካች ማሕበር ለሦስት ዓመት ያሕል የአስተዳደር አካል የሌለው በመሆኑ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 531 መሠረት ማሕበሩ ሊፈርስ ይገባል በማለት ውሳኔ ሠጥቷል፡፡ አመልካቾች ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን በመመርመር የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት አጽንቶታል፡፡

አመልካቾች ሐምሌ 21 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይህን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ሲሆን ይዘቱም፡- በስር ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር በ1ኛ አመልካች እና በተጠሪ መካከል በተደረገው ውል መሰረት የተጠሪን ጥቅም ለማስጠበቅ የሚያስችሉ ስራዎችን ለመስራት የማህበሩ ም/ስራ አስኪያጅ እና የስር

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ጣልቃ ገቦች ዝግጁ መሆናቸውን ከመግለጻቸውም በላይ ከተጠሪ ጋር ስምምነት ደርሰው እንደነበር ያስረዱ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ መሰረት ማድረግ የነበረበት የተጠሪን መብት ለማስጠበቅ ማህበሩ ሊፈርስ ይገባዋል ወይስ አይገባውም የሚለውን መሆን ሲገባው ማህበሩ እንዲፈርስ የሚያደርግ ምክንያት አለ ወይስ የለም የሚል ጭብጥ መያዙ የተከራካሪውን ክርክር ያልተከተለ በመሆኑ ተገቢነት የሌለው ነው፣ ለክሱ ምክንያት የሆነው ጉዳይ የተፈጠረው ማህበሩ ቤት ገንብቶ ለ 3ኛ ወገኖች ለመሸጥ በገባው ውል መሰረት በመሆኑ ለተጠሪም ጥቅም የሚያስገኘው ሆነ የ3ኛ ወገኖች ጥቅም የሚጠበቀው ማህበሩ ህልውናው ተጠብቆ በተቋቋመበት ዓላማ እና ለ3ኛ ወገኖች በገባው ውል መሰረት ግንባታውን ቀጥሎ ቤቶቹን ለ3ኛ ወገኖች በውሉ መሰረት ማስረከብ ሲችል ብቻ ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤቱ በአመልካቾች የቀረበውን ክርክር ማህበሩ ከተቋቋመበት ዓላማና ለሀገርም ሆነ ለ3ኛ ወገኖች የሚያበረክተውን ቀላል የማይባል አስተዋፅኦ በጥንቃቄ ሳይመረምር የሰጠው ውሰኔ የህግ መሰረት የሌለው ነው፣ ማህበሩ የተጓደሉበትን አመራሮች በመምረጥ ወደ ስራ እንዳይገባ እንቅፋት የፈጠረው እራሱ ተጠሪ ሆኖ እያለ በዚህ ምክንያት ማህበሩ እንዲፈርስ መጠየቁ ከቅን ልቡና ውጪ ከመሆኑም በላይ አንድ ማህበር እንዲፈርስ ሊያደርጉ ከሚችሉ በህጉ ከተቀመጡ ምክንያቶች ውጪ ነው፤ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የሰበር ሰሚው ችሎትም የአመልካቾችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ የአሁን ተጠሪ 1ኛ አመልካች የሆነው ማህበር ባለአክሲዮን ባልሆነበት ማህበሩ እንዲፈርስ የሰጠው ምክንያትም ማሕበሩን ለማስፈረስ የሚያስችል በቂ ምክንያት መሆን አለመሆኑ ሊመረመር የሚገባው በመሆኑ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት አዟል፡፡ ተጠሪ ሰኔ 24 ቀን 2016 ዓ.ም የሰጠው መልስ ይዘት በአጭሩ፡- 1ኛ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት በሌለበት የታየ በመሆኑና በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 78 መሠረት አመልክቶ ያልተከራከረ በመሆኑ ይግባኝ ሆነ የሰበር አቤቱታ ሊያቀርብ አይገባም፣ 1ኛ አመልካች አስፈላጊ የሆነ አስተዳደር አካል የሌለው እና የተቋቋመበትን የንግድ ስራ ዓላማ ለማሳካት ያልቻለ ማህበር በባለአክሲዮን ወይም በገንዘብ ጠያቂ በሚቀርብ አቤቱታ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሊፈርስ እንደሚችል በህጉ የተደነገገ በመሆኑ ተጠሪ የማህበሩ አባል ባልሆንም ማህበሩ እንዲፈርስ ዳኝነት የመጠየቅ መብትና ጥቅም አለኝ፣ በስር ፍርድ ቤት ህልውና የሌለው ማህበር እንዲፈርስ የተሰጠው ውሳኔ ለህብረተሰቡም ፣ለግብር ሰብሳቢውም ሆነ ለአበዳሪ የሚጠቅም እንጂ የሚጎዳ ውሳኔ አይደለም፣ በወራሾች በተፈጠረው አለመግባባት ምክንያት ማህበሩ አስተዳዳሪ ሳይኖረው ከ3 ዓመት በላይ መቆየቱ ማህበሩ ህልውና የሌለው በመሆኑ የሚያሳይ በመሆኑ በስር ፍርድ ቤት ማህበሩ እንዲፈርስ የተሰጠው ውሳኔ በቂ ምክንያት በመሆኑ የአመልካቾች መከራከርያ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም፡፡በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡ አመልካቾች በሰጡት የመልስ መልስ ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የግራ ቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ህጎች ጋር በማገናዝብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

በዚህ ችሎት የተያዘውን ጭብጥ መሠረት አድርገን ሥረ-ነገሩን ከመመርመራችን በፊት ተጠሪ በሰበር መልሱ ከፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 78 አንጻር ያቀረበውን መቃወሚያ አስቀድመን ተመልክተናል፡፡ 1ኛ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ጉዳዩ በሌለበት ታይቷል፡፡ ጉዳዩ በሌለበት የታየ ተከራካሪ ሁለት አማራጮች አሉት፤ አንደኛው ጉዳዩ ባለበት እንዲታይ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 78 በተመለከተው መስፈርት መሠረት አቤቱታ አቅርቦ ወደክርክሩ መግባትና መብቱን ማስከበር ነው፡፡ በዚህ አግባብ መብቱ ማስከበር ያልቻለ ወይም ወደክርክሩ ለመግባት ያልፈለገ ተከሳሽ በቀጥታ መብቱን በነካው ውሳኔ ላይ ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው፡፡ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ.ቁ. 320 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሠረት ተከራካሪ የሆነ ወገን ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው፡፡ በይግባኝ ሆነ በሰበር የሚያቀርበው ክርክር ወሰን በሥነ-ሥርዓት ሕጉ ማዕቀፍ የሚመረመር ሆኖ ጉዳዩ በሥር ፍርድ ቤት በሌለበት መታየቱ ብቻውን ይግባኝ ሆነ የሰበር አቤቱታ ከማቅረብ የሚከለክል ባለመሆኑ በዚህ ረገድ ተጠሪ ያቀረበውን መቃወሚያ አልተቀበልነውም፡፡

ወደዋናው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ 1ኛ አመልካች የሆነው ዶ/ር ክንዴ ካሰኝ እና ቤተሰቦቹ ሕንጻ ሥራ ተቋራጭ ኃ/የተ/የግል ማሕበር እንዲፈርስ የጠየቀ ሲሆን የንግድ ማህበሮች ከተቋቋሙ በኋላ እንደየአግባብነቱ በማህበርተኞቹ ስምምነት፣ በሕግ በተመለከተው ምክንያትና በፍርድ ቤት ውሳኔ ሊፈርሱ የሚችሉ ናቸው፡፡ በኢፌዴሪ የንግድ ሕግ ስለ ንግድ ማህበሮች በጠቅላላው በሚናገረው ክፍል የሚገኘው ቁጥር 181 ማህበር በሕግ፣ በስምምነት ወይም በፍርድ ቤት አማካኝነት የሚፈርስበትን ምክንያቶች ያመለክታል፡፡ ኃላፊነቱ የተወሰነ የንግድ ማሕበር በፍርድ ቤት ሊፈርስ የሚችለው በንግድ ሕጉ አንቀጽ 181 /4 እና 5/ እና 531 እንደተመለከተው የማሕበሩ አባላት ወይም ገንዘብ ጠያቂ ማሕበሩ እንዲፈርስ ሲያመልክቱ ወይም ማሕበሩ መክሰሩ በፍርድ ቤት ሲወሰን ነው፡፡ አንድ ማህበር እንዲፈርስ ጥያቄ ስለቀረበ ብቻ እንዲፈርስ ውሳኔ ሊሰጥ እንደማይችል እና ማህበሩ እንዲፈርስ ለመወሰን የሚያበቃ ምክንያት መኖሩን ፍርድ ቤቶች የማረጋገጥ ኃላፊነት እንዳለባቸው ከድንጋጌዎቹ ይዘት መረዳትይቻላል፣ ማህበራት ተገቢው የሕግ ጥበቃ ተደርጎላቸው ለአገር ኢኮኖሚ የሚያበረክቱት ሚና ግንዛቤ ውስጥ ገብቶ ሊመረመር የሚገባው ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ 1ኛ አመልካች የሆነው ዶ/ር ክንዴ ካሰኝ እና ቤተሰቦቹ ሕንጻ ሥራ ተቋራጭ ኃ/የተ/የግል ማሕበር እንዲፈርስ የጠየቀው ከማሕበሩ ጋር ነሀሴ 22 ቀን 2005 ዓ/ም የተደረገ የንብረት አስተዳደርና የሪል እስቴት ልማት ማኔጅመንት ውል ማድረጉንና የ1ኛ አመልካች ማሕበር ሥራ-አስኪያጅና ከፍተኛ የአክሲዮን ባለድርሻ የነበሩት ዶ/ር ክንዴ ካሰኝ ከሞቱ ጀምሮ ማሕበሩን የሚያስተዳድር አመራር መሰየም አልቻሉም፣ በዚህም ምክንያት በቂርቆስ ክፍለከተማ ወረዳ 7 በሚገኘው ይዞታው ላይ የተጀመረውን ግንባታ ለማጠናቀቅና ተጠሪ ለሦስተኛ ወገኖች የገባውን የውል ግዴታ ለመወጣት አልተቻለም፣ ፕሮጀክቱ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በመቆሙ ምክንያት ተጠያቂነት እየመጣብኝ ነው፣ ከፕሮጀክቱ ላገኘው የሚገባኝን ጥቅም አጥቻለሁ፣ በንግድ ሕጉ መሠረት ማሕበሩ የተቋቋመበትን ዓላማ መፈጸም ካልቻለ ወይም አስፈላጊ የሆነ የአስተዳደር አካል ከሌለው በገንዘብ ጠያቂ በሚቀርብ ጥያቄ ሊፈርስ ይችላል፡፡ ስለሆነም 1ኛ አመልካች ማሕበር እንዲፈርስ እንዲወሰን ዳኝነት ጠይቋል፡፡ 1ኛ አመልካች ጉዳዩ በስር ፍርድ ቤት በሌለበት የታየ ሲሆን የአክሲዮን ድርሻ ያላቸው ከ2ኛ-4ኛ የተመለከቱት አመልካቾች በክርክሩ ጣልቃ በመግባት የተከራከሩ ሲሆን የሥር ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ከ1ኛ አመልካች ጋር በገባው ውል መሠረት 57% ትርፍ ማግኘት የሚገባው የነበረ በመሆኑ ገንዘብ ጠያቂ መሆኑን ያሳያል፣ 1ኛ አመልካች ማሕበር ለሦስት ዓመት ያሕል  የአስተዳደር አካል የሌለው በመሆኑ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 531 መሠረት ማሕበሩ ሊፈርስ ይገባል በማለት ወስነዋል፡፡

በንግድ ሕጉ አንቀጽ 531 መሠረት ማሕበሩ አስፈላጊ የሆነ የአስተዳደር አካል የሌለው እንደሆነ በባለአክሲዮን ወይም በገንዘብ ጠያቂ በሚቀርብ ጥያቄ በፍርድ ቤት ሊፈርስ እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ ተጠሪ ክሱን ያቀረበው የ1ኛ አመልካች ማሕበር ባለአክሲዮን ባልሆንም ገንዘብ ጠያቂ ነኝ በሚል ነው፡፡ በንግድ ሕጉ ከማሕበሩ አንጻር 3ኛ ወገን የሆኑት ገንዘብ ጠያቂዎች ማሕበሩ ላይ የሚጠይቁት ገንዘብ ሲኖር ጥቅማቸውን ለመጠበቅ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኙት መብታቸውን ለማስከበር የተዘረጋ ሥርዓት ነው፤ተጠሪ ከ1ኛ አመልካች ጋር በጋራ ሪል እስቴት ለማልማት የውል ግዴታ የገባ ድርጅት ነው፡፡ ተጠሪ 1ኛ አመልካች ማሕበር ላይ የሚጠይቀው ገንዘብ መኖሩን በክሱ ሆነ በክርክሩ ሂደት አላሳየም፣ የተጠሪ መከራከሪያ ሆኖ የቀረበውና የሥር ፍርድ ቤቶች የተቀበሉት ተጠሪ ከ1ኛ አመልካች ጋር በገባው ውል መሠረት 57% ትርፍ ማግኘት የሚገባው የነበረ በመሆኑ ገንዘብ ጠያቂ መሆኑን ያሳያል በሚል ነው፡፡ ተጠሪ የውል ግዴታ የገባ ሲሆን ሥራው ትርፍ የሚያስገኝ ከሆነ ወጪውና ገቢው ተሰልቶ ውሉ ሲጠናቀቅ የሚታወቅ ነው፤ ትርፍ ከተገኘም ተጠሪን ሆነ 1ኛ አመልካችን በጋራ የሚጠቅም እንጂ ተጠሪን 1ኛ አመልካች ላይ ገንዘብ ጠያቂ አያደርገውም፡፡ አሁን ባለበት ሁኔታ ተጠሪ ከ1ኛ አመልካች ላይ የሚጠይቀው የታወቀ ገንዘብ የለም፣ የ1ኛ ማሕበር ሕልውና መቀጠልም ጉዳት የሚያስከትልበት መሆኑን አላሳየም፤ ስለሆነም ተጠሪ 1ኛ አመልካች ማሕበር እንዲፈርስ ለመጠየቅ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 531 አግባብ ገንዘብ ጠያቂ ስለመሆኑ ባላሳየበት አግባብ 1ኛ አመልካች ማሕበር እንዲፈርስ መወሰኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 300292 ግንቦት 30 ቀን 2015 ዓ/ም እና የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 01259 ታህሳስ 13 ቀን 2015 ዓ/ም የሠጡት በሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1)(ለ) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. 1ኛ አመልካች ማሕበር ሊፈርስ አይገባም ተብሎ ተወስኗል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

3. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

- ❖ የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- ❖ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ/ጋ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መዝገብ ቁጥር 251383

ጥቅምት 07 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች፡- ወ/ሮ አልማዝ አባተ -ቀርበዋል

ተጠሪ፡- አቶ ከበደ ሀብተማርያም -ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የባልና ሚስት የንብረት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክሱ በቀረበበት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ አመልካች በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት፡- ከተጠሪ ጋር የነበራቸው ጋብቻ በፍርድ ቤት በተላለፈ የፍቺ ውሳኔ መፍረሱን ተከትሎ የንብረት ክፍፍል አቤቱታ አቅርበው ፍርድ ቤት ውሳኔ አስተላልፏል፡፡ ይሁን እንጅ የንብረት ክፍፍል ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ ተጠሪ ለኮንዶሚኒየም ቤት ግዥ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ገንዘብ ሲቆጥቡ እንደነበረ ያወቁት የንብረት ክፍፍል ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ መሆኑን ፤ በዚህ የተቆጠበ ገንዘብ መነሻነትም ተጠሪ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ከተማ ኮዬ ፈጬ ሳይት ባለ አንድ መኝታ ቤት የደረሳቸው መሆኑን ጠቅሰው ገንዘቡ የተቆጠበው ግራ ቀኙ በጋብቻ ውስጥ እያሉ በመሆኑ ቤቱ የጋራ

ነው ተብሎ ድርሻቸው እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መልስ አመልካች ቀደም ብሎ ባቀረቡት የንብረት ክፍፍል ክስ በባንክ የተቆጠበውን ገንዘብ ድርሻቸው እንዲወሰንላቸው ጠይቀው ፍርድ ቤቱም ጋብቻቸው እስከፈረሰበት ጊዜ ድረስ የተቆጠበውን ብር 10,150.56 (አስር ሺ አንድ መቶ ሃምሳ ብር ከሃምሳ ስድስት ሳንቲም) እኩል እንዲካፈሉ የተወሰነ በመሆኑ እና ግንቦት 10 ቀን 2014 ዓ.ም ተመሳሳይ አቤቱታ አቅርበው ውደቅ ስለተደረገባቸው በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ ድጋሚ ክስ ማቅረብ አይችሉም በማለት የቀረበው ክስ ውድቅ እንዲሆን ተከራካረዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም አመልካች በተጠሪ ስም በባንክ ገንዘብ ይቆጠብ እንደነበር ያወቁት የንብረት ክፍፍል ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ መሆን አለመሆኑን፤ ክሱ በድጋሚ የቀረበ ነው ወይስ አይደለም? የሚሉ ጭብጦችን ይዞ መዝገቡን መርምሮ በሰጠው ውሳኔ አመልካች ተጠሪ ለኮንዶሚኒየም ቤቱ ግገር በባንክ ገንዘብ ይቆጥቡ እንደነበር የክፍፍል ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ያውቁ የነበረ መሆኑን፤ቀደም ብሎ አመልካች ባቀረቡት የንብረት ክፍፍል ጥያቄ መነሻነት አከራካሪው ኮንዶሚኒየም ቤት ለተጠሪ በዕጣ ከመድረሱ በፊት በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለኮንዶሚኒየም ግገር የተቆጠበውን ገንዘብ 10,150.56(አስር ሺ አንድ መቶ ሃምሳ ብር ከሃምሳ ስድስት ሳንቲም) ግራ ቀኙ እኩል እንዲካፈሉት ጥቅምት 13 ቀን 2015 ዓ.ም መወሰኑን ጠቅሶ አመልካች የመጨረሻ ውሳኔ ባገኘ ጉዳይ ላይ ድጋሚ ክስ ለማቅረብ አይችሉም በማለት አመልካች በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ኮዬ ፈጬ ሳይት የሚገኘውን ባለ አንድ መኝታ ቤት ለመካፈል ያቀረቡትን ክስ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 244/2(ለ) መሰረት ውደቅ ነው በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ያቀረቡትን የይግባኝ አቤቱታ የይግባኝ ሰሚው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

የሰበር ቅሬታው የቀረበው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ብይን እንዲሁም የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል በሰበር ሰሚው ችሎት ታይቶ እንዲታረም ሲሆን የሰበር ቅሬታው ይዘት በአጭሩ፡- አመልካችና ተጠሪ በጋብቻ ሲኖሩ ለኮንዶሚኒየም ግገር የሚሆን ገንዘብ በባንክ ሲቆጥቡ ቆይተው የደረሳቸውን ባለ አንድ መኝታ ቤት በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ኮዬ ፈጬ ሳይት በአሁኑ አጠራር ሸገር ከተማ ኮዬ ፈጬ ክፍለ ከተማ ወዴሳ ወረዳ ሳይት ፕሮጀክት16 የሚገኘው ቤት የጋራ መሆኑን፤ሌሎች ንብረቶችን በሽማግሌ ተከፋፍለው የጋራ መኖሪያ ቤት መብት የማስተላለፍ የመተማመኛ ስምምነት ውል የፈረሙ ቢሆንም ተጠሪ እንደ ውሉ ለመፈጸም ፈቃደኛ በለመሆናቸው የሥር ፍርድ ቤት ውሉን ሳያይ እና በመተማመኛ በስምምነቱ ላይ የተመለከቱ ምስክሮችን ሳይሰማ መወሰኑ፤የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይሕን ውሳኔ ማጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሮ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ኮዬ ፈጬ ሳይት በአሁኑ አጠራር ሸገር ከተማ ኮዬ ፈጬ ክፍለ ከተማ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

ወዴሳ ወረዳ ሳይት ፕሮጀክት16 የሚገኘው ባለ አንድ መኝታ ቤት የጋራ ነው ተብሎ እንዲወሰን ጠይቀዋል፡፡

በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 6/1 መሠረት ለሰበር ሰሚው ችሎቱ የተመራው አቤቱታ በሰበር ሰሚ ችሎቱ ተመርምሮ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ክስ ያቀረቡት የግራ ቀኙ ጋብቻ በፍቺ ቀሪ ሆኖ ለጋራ መኖሪያ ቤት ሲቆጠብ የነበረው ገንዘብ እንዲካፈሉ ውሳኔ የተሰጠ ቢሆንም በውሳኔው መሠረት ክፍፍል ከመፈፀሙ በፊት የጋራ መኖሪያ ቤት ዕጣ ለተጠሪ በመውጣቱ ምክንያት ቤቱ የጋራ ሀብት ነው ተብሎ እንዲያካፍሏቸው ያቀረቡት ክስ ቀድሞ ውሳኔ ባገኘ ጉዳይ ላይ በድጋሚ የቀረበው ነው በሚል ውድቅ የተደረገበት አግባብ ከፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 5/1 አንፃር ለመመርመር የሰር አቤቱታው ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ በሰጡት መልስ፡- በአመልካችና ተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ በ2009 ዓ.ም ፈርሶ በ2011 ዓ.ም የንብረት ክፍፍል አድርገው ከተለያዩ በኋላ በ2012 ዓ.ም የጋራ መኖሪያ ቤቱ ዕጣ መውጣቱን ፤የፍቺ ውጤት በሆነው የንብረት ክፍፍል ክርክር ለኮንዶሚኒየም ቤቱ ግዥ በባንክ ሲቆጥቡ የቆዩትን ገንዘብ እኩል እንዲካፈሉ በተሰጠው ውሳኔ መሰረት ግራ ቀኙ ተከፋፍለው ከተለያዩ እና አፈፃፀሙ ካበቃ በኋላ ተጠሪ በቆጠቡት ገብዘብ ያቀረቡት የይገባኛል ክስ የሕግ መሠረት የለውም፡፡ አመልካች ለአከራካሪው ኮንዶሚኒየም ቤት ግዥ ሲቆጠብ የነበረውን ገንዘብ እንዲካፈሉ የተላለፈውን ውሳኔ በመቃወም ያቀረቡት ክርክር በሌለበት በድጋሚ አቤቱታ ሊቀርብ አይገባም ተብሎ ውደቅ መደረጉ ተገቢ መሆኑን ጠቅሰው ዕጣው የደረሰው የንብረት ክፍፍል ከተደረገ ከ3(ሶስት) ዓመት በኋላ ሆኖእያለ ከንብረት ክፍፍል በፊት ነው በማለት አመልካች ያቀረበችው ክርክር ሀሰት ስለሆነ በአንድ በኩል የሚገባት ንብረት ተካፍላ እንደሄደች እየገለፀች በሌላ በኩል ደግሞ ንብረቱ መኖሩን አሁን እንደተረዳች የሚታቀርበው አቤቱታ እርስ በርሱ ስለሚጣረስ የሰበር ቅሬታው ውደቅ ሆኖ ለሰበር አቤቱታው ምክንያት የሆነው ውሳኔ እንዲፀናላቸው ጠይቀዋል፡፤

አመልካችም የሰበር አቤቱታውቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለ መልኩ የተመለከተው የግራ ቀኝ ክርክር እና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ውሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንፃር የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለው ሕግ እና የሰበር ሰሚ ችሎቱ በጉዳዩ ላይ ከሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በመሰረቱ ክስ ወይም የክስ መዝገብ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ምክንያት ሊዘጋ የሚችለው በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ሆኖ ሊቀርቡ ይችላሉ ተብለው ከተዘረዘሩት ምክንያቶች አንዱ መኖሩ ሲረጋገጥ ነው፡፡ (በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

244/2 ይመለከቷል)፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማስረጃ የተደገፈና ተገቢ ሆኖ ከተገኘ እና ፍርድ ቤት ከተቀበለው ክርክሩን ይቋርጠዋል፡፡ የፍትሐ ብሔር የክርክር አመራር ሥርዓት ዓይነተኛ ዓላማ ክርክሮች በአነስተኛ ወጪ፣ ጊዜ እና ጉልበት እልባት እንዲያገኙ ማስቻል ሲሆን ሂደቱም በተወሰነ ደረጃ ላይ ሲደርስ መቋጫ እንዲኖረው ለማድረግ መሆኑ እሙን ነው፡፡ የፍትሐ ብሔር ክርክር አንድ ደረጃ ላይ ሲደርስ እልባት እንዲደረግበት በማቀድ ከተደነገጉት የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ጽንሰ ሃሳቦች አንዱ የመጨረሻ ፍርድ ያገኙ ጉዳዮች ላይ ዳግም ክስ ሊቀርብ አይገባም /Res judicata/ የሚለው ሲሆን ይህ ጽንሰ ሀሣብ በ1958ቱ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ በቁጥር 5/1 ድንጋጌ ስር በግልጽ ተቀምጦ እናገኘዋለን፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የመጨረሻ ፍርድ ያገኙ ጉዳዮች ማለት በማናቸውም መልክ በሕግ በተቋቋመ ፍርድ ቤት ወይም የዳኝነት ስልጣን በተሰጠው አካል ቀርበው የመጨረሻ ውሳኔ ያገኙ ጉዳዮችን የሚሸፍን መሆኑንና በፍርድ፣ በብይን፣ በውሣኔ፣ በትአዛዝ፣ ወይም ጊዜያዊ አገልግሎት ባልሆነ ትእዛዝ የመጨረሻ ውጤት አግኝተው በሌላ መልክ ማንቀሣቀስ የማይቻል የክርክር ነጥቦችን ሁሉ የሚያጠቃልል ጉዳይ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 5/1 ሥር እንደተደነገገው አንድ ጉዳይ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው ለማለት መረጋገጥ ያለባቸው አራት መሰረታዊ ነጥቦች ናቸው፡፡ እነሱም ጉዳዩ በህግ ስልጣን የተሰጠው አካል የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ መሆን አለመሆኑ፣ቀድሞ የቀረበው ክስ ስረ ነገር እና ለውሳኔ መሰረት የተደረገው ጭብጥ አሁን ከቀረበው ክስ ጋር አንድ ወይም ተመሳሳይ መሆን አለመሆኑ፣እንዲሁም ተከራካሪዎቹ አንድ መሆን ወይም ከቀድሞ ተከራካረዎች መብት ያገኙ ሶስተኛ ወገኖች ከሆኑ በዚያው ነገር ሁለተኛ ክስ ማቅረብ እንደማይችል ከፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት 5/1 እና 244/2)ለ ድንጋጌዎች ይዘት ፣ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 36780 ላይ መጋቢት 03 ቀን 2001 ዓም በዋለው ችሎት ከሰጠው ገዥ ውሳኔም መረዳት ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበራቸው ጋብቻ በፍርድ ቤት በተላለፈ የፍቺ ውሳኔ ደርሶ የንብረት ክፍፍል አቤቱታ ቀርቦ ውሳኔ አግኝቷል፡፡ የንብረት ክፍፍል ውሳኔ ከተሰጠባቸው ንብረቶች ውስጥ ለአከራካሪው ኮንዶሚኒየም ቤት ግዥ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሲቆጠብ የነበረው ብር 10,150.56(አስር ሺ አንድ መቶ ሃምሳ ብር ከሃምሳ ስድስት ሳንቲም) አንዱ ሲሆን ግራ ቀኙ ይሕንን ገንዘብ እኩል እንዲካፈሉት የተወሰነ ቢሆንም ክፍፍሉ ከመፈፀሙ በፊት የኮንዶሚኒየም ቤት ዕጣ ወጥቶ አስቀድሞ የጋራ ነው ተብሎ የተወሰነው ገንዘብ ወደ ሌላ ንብረት ተቀይሮ ቤት ሆኗል፡፡ ለኮንዶሚኒየም ቤት በዕጣ መገኘት ለግዥው የሚውል ገንዘብ ማጠራቀም ቅደሜ ሁኔታ በመሆኑ አስቀድሞ ግራ ቀኙ እንዲካፈሉ የተወሰነው ለኮንዶሚኒየም ቤቱ ግዥ የተቆጠበውን ገንዘብ ሲሆን አመልካች አሁን ለመካፈል እየጠየቁ ያሉት ንብረት በፊት እንዲካፈሉ በተወሰነው ገንዘብ ግዥ ከፍቺ ውሳኔ በኋላ የተፈራ ኮንዶሚኒየም ቤት በመሆኑ የክርክሩ ጭብጥ የተለያየ ሆኖእያለ ዳግም የቀረበ ነው መባሉ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት 5/1/ ፣ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ችሎት በመዝገብ ቁጥር 36780 የሰጠውን ውሳኔ የሚቃረን መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

**ውሳኔ**

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 119479 የካቲት 21 ቀን 20115 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፤ እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 306538 ግንቦት 24 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ብይን በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ- ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 9/1(ለ) መሠረት ተሸሯል።
2. አመልካች በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ኮዬ ፈጬ ሳይት በአሁኑ አጠራር ሸገር ከተማ ኮዬ ፈጬ ክፍለ ከተማ ወዴሳ ወረዳ ሳይት ፕሮጀክት16 የሚገኘው ባለ አንድ መኝታ ኮንዶሚኒየም ቤት የሚስትነት ድርሻቸው እንዲሰጣቸው ያቀረቡት ክስ ዳግመኛ የቀረበ አይደለም፡፡
3. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በውሳኔ የዘጋውን የመዝገብ ቁጥር 119479 አንቀሳቅሶ በፍሬ ነገሩ ላይ አከራክሮ ሕጋዊ ውሳኔ እንዲሰጥ በሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 9/2 መሠረት መዝገቡ ተመልሶለታል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰመ/ቁ. 251537

ጥቅምት 27 ቀን 2017ዓ/ም

ዳኞች ፡- ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ብርሃኑ መንግሥቱ

ማርታ ተካ

አመልካች - የአማራ ክልል መንግሥት ፍትህ ቢሮ - ዐቃቤ ሕግ

ተጠሪ - ጌታቸው አበራ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ ተጠሪ ከቀረበባቸዉ የወንጀል ክስ በነጻ እንዲሰናበቱ በመወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል የቀረበ የሰበር አቤቱታ የሚመለከት ነዉ፡፡የክሱ ይዘት በአጭሩ - በቀን 06/02/2014ዓ.ም ከጠዋቱ በግምት 3፡00 ሰዓት ሲሆን በወልድያ ከተማ 06 ቀበሌ አንድ ኮምፒውተር፣አንድ ፕሪንተር፣ሁለት በረንዳ መስሪያ ብረት፣ አንድ የመከላከያ ቲሸርት፣አንድ የመከላከያ የዝናብ ልብስ፣አንድ የመከላከያ የውሃ ኮዳ ከተከራየው ቤት በፍተሻ የተገኘበት በመሆኑ እና በወልድያ ከተማ 06 ቀበሌ ልዩ ቦታው አረጉ ወፍጮ ከተባለ ቦታ ካለው ኮንቴነር ሁለት የብረት መበየጃ ማሽን ጠቅላላዉ ዋጋቸዉ ብር 41,200.00(አርባ አንድ

ማስታወሻ፡ - ይህ የ ሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነ ድ ለ ጥናት ና ምርምር ሥራ ወይምለ ግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ሺህ ሁለት መቶ ብር) የሚገመት የመንግስት ንብረት ሰርቆ የተገኘ በመሆኑ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 669(3/ለ) ስር የተደነገገዉን በመተላለፍ በፈጸመዉ በከባድ ስርቆት ወንጀል ተከሷል የሚል ነዉ፡፡

የወልድያ ወረዳ ፍርድ ቤት ለተጠሪ የክስ ማመልከቻዉ እንዲደርሰዉ አድርጎ አንብቦላቸዉ የወንጀል ድርጊቱን አልፈጸምኩም በመላት ክዶ በመከራከሩ ዐቃቤ ሕግ ምስክሮቹን አቅርቦ አሰምቷል፡፡ ምስክሮቹም የሰላም ኮሚቴ በጥቆማ ተጠሪ የሚኖርበትን ቤት በመበርበር በክሱ የተጠቀሱትን ዕቃዎች ማግኘታቸዉን መስክረዋል፡፡ይህንን ተከትሎ ፍርድ ቤቱ ተጠሪ በተከሰሰበት ድንጋጌ ስር ክሱን እንዲከላከል አዝዟል፡፡ በመቀጠል የተጠሪ የመከላከያ ምስክሮቹን አቅርቦ ያሰማ ሲሆን 1ኛ መከላከያ ምስክር ተጠሪ የገዛሁትን ንብረት ጭነዉ ወስዱብኝ ሲል ሰምቻለሁ እንጂ የገዛዉን ንብረት አላየሁም በማለት ሲመሰክር 2ኛ እና 3ኛ መከላከያ ምስክሮችም ተጠሪ ዕቃ ሲገዛ አላየንም ምን አደረገ ተብሎ እንደተከሰሰ አናዉቅም በማለት መስክረዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 0202409 ላይ በቀን 28/02/2015ዓ/ም በሰጠዉ ፍርድ ተጠሪ በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ የተረጋገጠበትን የስርቆት ወንጀል ያለመፈጸሙን በመከላከያ ምስክሮቹ ያላስተባበለ በመሆኑ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 669(3/ለ) ስር ጥፋተኛ ነዉ ሲል ወስኗል፡፡በመቀጠል የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት በመመርመር ተጠሪ ብሎ በ5 (አምስት) ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡

ተጠሪ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ውድቅ ተደረጎበታል፡፡በመቀጠልም ተጠሪ የሰበር አቤቱታዉን ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በማቅረቡ ችሎቱ በመ/ቁጥር 0336933 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 09/09/2015ዓ/ም በዋለዉ ችሎት በአብላጫ ድምጽ በሰጠዉ ዉሳኔ አንድ ወንጀል የሚያስቀጣው ወንጀሉ መፈፀሙን በበቂ እና አሳማኝ በሆነ ማስረጃ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 23/4 ስር ተመልክቷል፡፡ዓቃቤ ሕግ ክስ ያቀረበበት ድርጊት ስለመፈፀሙ ባቀረባቸው ማስረጃዎች አሳማኝ እና በቂ በሆነ ሁኔታ የማስረዳት ግዴታ አለበት፡፡በወንጀል ሕግ አንቀጽ 669/3 የተቀመጡት የወንጀል ማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮች መውሰድ እና የሌላ ሰው ንብረት የሚሉት ናቸው፡፡የቀረቡት የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች አመልካች በሌለበት ፍተሻ ሲደረግ ንብረቶቹ በተከራየው ቤት ውስጥ እና ኮንቴነር ውስጥ መገኘታቸውን እንጂ ንብረቶቹ ከየት ፣እንዴት እንደተገኙ እና ከማን እንደመጡ በበቂ እና አሳማኝ በሆነ ሁኔታ አላስረዱም፡፡ተጠሪ በተከራየው ቤት ተገኙ የተባሉትን እና በዓቃቤ ሕግ ክስ ላይ የተገለፁትን ንብረቶች ይዞ ሲሄድም ሆነ በቤቱ ማስቀመጡን፤ለምን አላማ እንደመጡ፤እንዲሁም ንብረቶቹ የማን እንደሆኑ፤ በማን እንደመጡ፤ ለምን አላማ እንደመጡ አላስረዱም፡፡ዓቃቤ ሕግ ያቀረባቸው የሰነድ ማስረጃዎችም ንብረቶቹ የማን እንደሆኑ አያረጋግጥም፡፡ከዚህ ባለፈም በተጠሪ ቤት ውስጥ ተገኙ የተባሉት አብዛኛዎቹ ንብረቶች በግለሰብ ቁጥጥር ስር ሊሆኑ የማይችሉ ስለመሆኑም አላረጋገጠም፡፡ በመሆኑም ተጠሪን ጥፋተኛ በማለት በ5 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ መወሰናቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው በማለት ተጠሪን በነፃ በማሰናበት በአብላጫ ድምፅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የልዩነት ሀሳቡ ተጠሪ በክሱ የተጠቀሱትን ንብረቶች አከማችቶ መገኘቱ ስለተረጋገጠ በወንጀል

ማሳ ታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ሕግ አንቀጽ 682/1 ወይም 682/3 ስር የተደነገገዉን የሚያቋቁም በመሆኑ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 113/2 መሰረት ተጠሪ የተከሰሰበትን ድንጋጌ በመለወጥ ጥፋተኛ መደረግ ነበረበት የሚል ነዉ፡፡

አመልካች በቀን 12/10/2015 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉ ከላይ በተመለከተዉ መሰረት የተሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚል ሲሆን ይዞቱ በአጭሩ - የክልሉ ሰበር የሰጠዉ ዉሳኔ የማስረጃ ምዘና ስህተት አለበት፡፡ተጠሪ ጥፋተኛ መባል ያለበት ድንጋጌ መቀየር ካለበትም በልዩነት ሀሳብ መሠረት ድንጋጌዉ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 682/1 ወይም 682/3 መሰረት ተቀይሮ ጥፋተኛ ተብሎ እንዲቀጣ ሊወሰን ሲገባ በነፃ እንዲሰናበት መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው፡፡

ችሎት የሰበር አቤቱታዉን እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉን ዉሳኔ በመመርመር የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በአብላጫ ድምጽ ዉሳኔ የደረሰበት ድምዳሜ አመልካች ስለመፈጸሙ በማስረጃ ከተረጋገጠዉ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች አንጻር በወንጀል ሕግ ቁጥር 23/2 የተደነገገዉንና ከዚህ ድንጋጌ እና ከማስረጃ ምዘና መርህ አተገባበር አንጻር በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት 38161 (ቅጽ 9) እና 89676(ቅጽ 17) ላይ የተሰጠዉን የሕግ ትርጉም የተከተለ መሆን አለመሆኑን ?የወንጀል ሕግ አንቀጽ 669(3/ለ) አፈጻጸም በተመለከተ በሰ/መ/ቁጥር 245531 (ያልታተመ) የተሰጠዉን የሕግ ትርጉም እንዲሁም አመልካች ስለመፈጸማቸዉ ከተመሰከረባቸዉ ድርጊት አንጻር በየትኛዉ የወንጀል ሕግ ጥፋተኛ ተብለዉ ሊቀጡ ይገባል የሚለዉን በተመለከተ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 113/2 የተደነገገዉንና ከዚህ ድንጋጌ አፈጻጸም ጋር በተያያዘ በሰ/መ/ቁጥር 45595 (ቅጽ 12) ላይ ከተሰጠዉ የሕግ ትርጉም አንጻር የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን እንዲመረመር ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ አዝዟል፡፡ለተጠሪ የተላከዉን መጥሪ አመልካች ማድረሱን ማስረጃ ያስረዳ ቢሆንም ተጠሪ በተሰጠዉ ቀነ ቀጠሮ ባለመቅረቡ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

ከላይ አጠር ባለ መልኩ የተገለጸዉ የግራ ቀኙን ክርክር እና በየደረጃዉ ባሉት የክልሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎችን የሚመለከት ሲሆን እኛም ከላይ የተጠቀሱትን ጭብጦች መሠረት በማድረግ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ በመሰረቱ በአገራችን የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሥርዓት መሰረት ሕገ-ወጥነቱና አስቀጪነቱ በሕግ የተደነገገዉን በማድረግ የሚፈጸም የወንጀል ድርጊት ወይም አል ድርጊት ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮችን በአንድነት በሚያሟላ አኳኋን መፈጸሙ በፍርድ ቤት የተረጋገጠበት ወንጀል ፈጻሚ በወንጀል ሕጉ እና አግባብነት ባለዉ ሌላ ሕግ የተደነገገዉን ቅጣት መቀጣት ይገባዋል፡፡ አንድ ሰው በወንጀል ደርጊት ተጠያቂ የሚሆነው የተከሰሰበትን ድርጊት ወንጀል አድርጎ በሚደነግገዉ ሕግ ላይ በተመለከተዉ መሠረት ድርጊቱን ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት መፈጸሙ በማስረጃ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 58 እና 59 ስር ተደንግጓል፡፡ በዚህ መልኩ ተከሳሹ ጥፋተኛ ሆኖ ሊቀጣ የሚችለዉ በወንጀል ሕጉ ልዩ ድንጋጌዎችና በሌላ ልዩ ሕግ በተለየ ሆኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ተከሳሹ

የተከሰሰበትን ወንጀል ስለመፈጸሙ ዐቃቤ ሕግ ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮችን በሚያሳይ አኳኋን በማስረጃ ሲያስረዳ ነዉ(የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23 ይመለከቷል)፡፡

በሌላ በኩል አንድ የወንጀል ክስ የቀረበበት ሰዉ በዐቃቤ ሕግ በኩል የተመሰረተበት የወንጀል ክስ ላይ በተመለከተዉ ዝርዝር መሰረት በማስረጃ ሳይረጋገጥ ቢቀርም የቀረበዉ ማስረጃ ከቀረበበት ክስ ያነሰ የወንጀል ድርጊት በተከሳሹ መፈጸሙን ያረጋገጠ እንደሆነ በዚህ መልኩ በተከሳሹ ስለመፈጸሙ በተረጋገጠዉ የወንጀል ድርጊት በተከሳሹ ላይ ክስ ባይቀርብም ፍርድ ቤቶች ተገቢዉን የሕግ ድንጋጌ ለይተዉ ተከሳሹ እንዲከላከል መበየን ወይም በማስተባበል መከላከል ካልቻለም የጥፋተኝነት ፍርድ መስጠት እንደሚችሉ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 113/2 ስር ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡ከዚህ ድንጋጌ አተገባበር ጋር በተያያዘ ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 45595 (ቅጽ 12) ፣ 234260 እና በሌሎች መዛግብት አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

አመልካች በተጠሪ ላይ ክሱን የመሰረተዉ ተጠሪ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 669(3/ለ) ስር የተደነገገዉን በመተላለፍ በክሱ ላይ የተጠቀሱትን ጠቅላላ ዋጋቸዉ ብር 41,200.00 የሆኑ የመንግስት ንብረቶች በመስረቅ በከባድ ስርቆት ወንጀል ፈጽሟል በሚል ነዉ፡፡አመልካች አቅርቦ ያሰማቸዉ ምስክሮች በወልድያ ከተማ ዉስጥ የነበረዉ ጦርነት ቆሞ የሰላም ኮሚቴ ሆነዉ ሲሰሩ በጥቆማ ተጠሪ የሚኖርበትን ቤት ሲበረብሩ በቤቱ ዉስጥ በክሱ የተጠቀሱትን የመንግሥት ንብረቶች ማግኘታቸዉን መመስከራቸዉን የስር ወረዳ ፍርድ ቤት አረጋግጧል፡፡ይህንን ተከትሎ ተጠሪ ክሱን እንዲከላከል የታዘዘ ቢሆንም ንብረቶቹን በሕግ አግባብ እንዳገኛቸዉና የግሉ እንደሆኑ በማስረዳት ማስተባበል እንዳልቻለ በመግለጽ ፍርድ ቤቱ ተጠሪን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 669(3/ለ) ስር ጥፋተኛ ነዉ በማለት ወስኖበታል፡፡ሆኖም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በዉሳኔዉ ላይ እንደገለጸዉ ተጠሪ የተከሰሰበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 669(3/ለ) የሚጠይቀዉን የሰዉን ንብረት የመዉሰድ ድርጊት ተጠሪ የፈጸመ ስለመሆኑ ዐቃቤ ሕግ ባቀረባቸዉ ምስክሮች እና የሰነድ ማስረጃ አላስረዳም፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ስለመፈጸሙ በማስረጃ የተረጋገጠዉ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገር ተጠሪ በሚኖርበት ቤት ዉስጥ ንብረትነታቸዉ የመንግሥት የሆኑ ዕቃዎችና አልባሳት መገኘታቸዉ ሲሆን ተጠሪ እነዚህ ንብረቶች የግል ንብረቶቹ እንደሆኑ ባቀረባቸዉ መከላከያ ማስረጃዎች በማስተባበል አለመከላከሉን በሕግ ማስረጃ የመመርመርና የመመዘን ሥልጣን የተሰጠዉ የወረዳ ፍርድ ቤት አረጋግጧል፡፡

ይህ ሰበር ችሎት በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 80(3/ሀ) ስር የተሰጠዉ ሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሀ-ሸ) እና 10/1 በተደነገገዉ መሠረት እንዲሁም የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 80(3/ለ)፣ በክልል ሕግጋተ መንግሥታት እና በየፍርድ ቤቶቻቸዉ አዋጆች ላይ በተደነገገዉ መሰረት የተመለከቱትን መሰረታዊ የሕግ ስህተቶችን የሚያርም ዉሳኔ

እንዲሰጡ ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በዚህ መሠረት የማስረጃ አቀራረብን፣ አግባብነትን፣ ተቀባይነትን እና ማስረጃ አቅርቦ አንድን ፍሬ ነገር የማስረዳት ሸክም መርህ (Production, relevancy, admissibility and burden of proof of evidence)እንዲሁም የማስረጃ ምዘናን ወይም የማስረዳት ደረጃን (standard of proof or weight of evidence) የሚመለከቱ መሰረታዊ መርሆዎች ተጥሶ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን እና በይግባኝ ሰሚነት በሚዳኙ ፍርድ ቤቶች የተሰጠ የመጨረሻ ዉሳኔ ካልሆነ በስተቀር ማስረጃ የመመርመርና የመመዘን ሥልጣን የተሰጣቸዉ ፍርድ ቤቶች ማስረጃ መርምረዉና መዝነዉ ያረጋገጡትን ፍሬ ነገር ወደ ጎን በመተዉ ማስረጃ መርምሮና መዝኖ የአንድን ፍሬ መነገር መኖር አለመኖር የማረጋገጥ ሥልጣን ለፌዴራልም ሆነ ለክልል ሰበር ችሎቶች አልተሰጣቸዉም፡፡

ከላይ እንደተመለከተዉ በሕግ ማስረጃ የመመርመርና የመመዘን ሥልጣን የተሰጠዉ የወረዳ ፍርድ ቤት በማስረጃ እንደተረጋገጠዉ እና በክልሉ ሰበር ችሎት በተሰጠ ዉሳኔ የልዩነት ሀሳባ ላይ እንደተገለጸዉ ተጠሪ በክሱ ላይ የተጠቀሱት እቃዎችና አልባሳት በወለድያ ከተማና አካባቢዉ በነበረዉ ጦርነት ምክንያት የተሰረቁ ወይም ሌላ ወንጀል የተፈጸመባቸዉ የመንግሥት ንብረቶች መሆናቸዉን ከዕቃዎቹና ከአልባሳቱ አይነት የተነሳ እያወቀ እነዚህን ዕቃዎችና አልባሳት በሚኖርበት ቤት ደብቆ ያስቀመጠ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡የወረዳዉ ፍርድ ቤት ከዚህ አንጻር በተጠሪ ላይ በተመሰረተዉ ክስ የተጠቀሰዉን የወንጀል ሕግ ድንጋጌ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 113/2 መሰረት ወደ ወንጀል ሕግ አንቀጽ 682/1 በመለወጥ በተጠሪ ላይ የጥፋተኝነት ፍርድ ማስተላለፍ ሲገባዉ ተጠሪ የሕዝብ ብጥብጥን ምክንያት በማድረግ ንብረቶቹን መስረቁ ሳይመሰከርበት ተጠሪን በተከሰሰበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 669(3/ለ) ስር ጥፋተኛ ነዉ ሲል መወሰኑ በማስረጃ የተረጋገጠዉ ግዚፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገር መሠረት ያላደረገ በመሆኑ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 23/2 ስር የተደነገገዉን፣ ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 113/2 እና ከማስረጃ ምዘና መርህ አተገባበር ጋር በተያያዘ ይህ ችሎት ካል በተጠቀሱ መዛግብት ላይ የሰጠዉን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሚቃረን በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተዉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በወረዳዉ ፍርድ ቤት በተሰጠዉን ዉሳኔ ላይ የተፈጸመዉን ተጠቃሹን ስህተት በዚሁ አግባብ ማረም ሲገባዉ ይግባኙን መሠረዙ ሊታረም የሚገባዉ ስህተት ነዉ፡፡

በተጨማሪም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ከላይ በተገለጸዉ መሰረት በተጠሪ ስለመፈጸሙ በማስረጃ የተረጋገጠዉን ግዙፋዊና ሞራላዊ ፍሬ ነገር መሠረት በማድረግ ድርጊቱን ወንጀል የሚያደርገዉን የወንጀል ሕግ ድንጋጌ በመለየት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 113/2 መሠረት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 682/1 መሠረት ጥፋተኛ ነዉ በማለት ቅጣቱንም ከዚህ አንጻር በማሻሻል መወሰን ነበረበት፡፡ሆኖም ማስረጃ የመመዘን ተግባር ዉስጥ በመግባት ንብረቶቹ ከየት ፣እንዴት እንደተገኙ እና ከማን እንደመጡ፣ ተጠሪ ንብረቶች ይዞ ሲሄድም ሆነ በቤቱ ማስቀመጡን፤ለምን አላማ እንደመጡ፤እንዲሁም ንብረቶቹ የማን እንደሆኑ

በበቂ እና አሳማኝ በሆነ ሁኔታ ዐቃቤ ሕግ በማስረጃ አላስረዳም በማለት የስር ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በመሻር ተጠሪ በነጻ እንዲሰናበት መወሰኑ ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 113/2 ፣ ከማስረጃ ምዘና መርህ አተገባበር ጋር በተያያዘ የተሰጠዉን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም እንዲሁም ማስረጃ በመመዘን የአንድ ፍሬ ነገር መኖር ያለመኖር ከማረጋገጥ አንጻር የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ሥልጣን የሌለዉ ከመሆኑ አኳያ ሲታይ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሀ እና ሸ) እና 10(1/ሐ) መሠረት ሊታረም የሚገባዉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡

ቅጣትን በተመለከተም የወንጀል ቅጣትና የጥንቃቄ እርምጃዎች የሚወሰነዉ በወንጀል ሕጉ ታላቅ ክፍል ስለወንጀል ቅጣት አወሳሰን የተደነገጉ መርሆዎችንና ሁኔታዎችን እንዲሁም ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው የሚደነግጉትን የልዩ ክፍሉ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ መሆኑን፣ የወንጀል አድራጊውን ግላዊ የአደገኛነት መጠን፣ ያለፈ የህይወት ታሪኩን፣ ወንጀል ለማድረግ ያነሣሡትን ምክንያቶችና የአሣቡን ዓላማ፣ የግል ኑሮውን ሁኔታ፣ የትምህርቱን ደረጃ፣ እንዲሁም የወንጀሉን ከባድነትና የአፈፃፀሙን ሁኔታዎች በማመዛዘን መሆኑን፣ የወንጀል ሕግ ልዩ ክፍል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነዉ ፍርድ ቤቱ በሕጉ የተመለከቱትን የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶችን በመያዝ እጅግ ቀላል ከሆነው ቅጣት አንስቶ እስከ ከባዱ ድረስ ያለውን በጥንቃቄ በመመርመር ለእያንዳንዱ ጉዳይ ተገቢ የሆነውን ቅጣት እንደሚወስን በወንጀል ሕጉ እና በቅጣት አወሳሰን መመሪያዉ ላይ የተመለከተዉ የቅጣት አወሳሳን ደንብ ያሳያል (የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 82-88 ይመለከቷል)፡፡በዚህ መሠረት በተጠሪ ተሸሽገዉ የተገኙ ንብረቶች ግምት ብር 41,200.00(አርባ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ብር) እና ንብረቶቹ የመንግሥት ንብረቶች መሆናቸዉን ከግምት በማስገባት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 682/1 ስር ከተደነገጉት አማራጭ ቅጣቶች መካከል ከአምስት ዓመት ጽኑ እስራት የማይበልጥ የሚለዉን የቅጣት አማራጭ ይዘናል፡፡ በመቀጠል ወንጀሉ ደረጃ ያልወጣለት በመሆኑ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሠረት ለቅጣቱ ደረጃ በማዉጣት ደረጃዉን መካከለኛ ደረጃ ላይ በመመደብ መነሻ ቅጣት 3 ዓመት ጽኑ እስራት ይዘናል፡፡ይህም በእርከን 14 ላይ የሚያርፍ ነዉ፡፡አመልካች በስር ፍርድ ቤት የቅጣት ማክበጃ እንዳላቀረበም፡፡ተጠሪ የቅጣት ማቅለያ ባያቀርብም የቀድሞ የዘወትር ጠባዩ መልካም እንደነበር ተቆጥሮ በስር ፍርድ ቤት የያዘለትን አንድ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት በመያዝ ቅጣቱን ከእርከን 14 ወደ እርከን 13 ዝቅ በማድረግ ችሎቱ በእርከኑ የተመለከተዉን ፍቅድ ሥልጣን ከግምት በማስገባት ተጠሪን ያርማል፤ መሰል ወንጀለኞችን ያስጠነቅቃል ብለን ባመንበት በ2 (ሁለት) ዓመት ከ3(ሦስት)ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጣ በማሻሻል ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ውሳኔ

1. የወልድያ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 0202409 ላይ በቀን 28/02/2015ዓ/ም የሰጠዉ የጥፋተኝነት እና የቅጣት ዉሳኔ እና የሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 0212060

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

ላይ በቀን 120/05/2015 ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 መሰረት ተሻሽለዋል፡፡

2. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 033633 ላይ በቀን 09/09/2015 ዓ/ም በአብላጫ ድምጽ የሰጠዉ ዉሳኔ በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 መሰረት ተሽሯል፡፡
3. ተጠሪ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 682/1 ስር ጥፋተኛ ነዉ ብለናል፡፡በዚህ መሠረት ተጠሪ ከዚህ ወንጀል ጋር በተያያዘ የታሰረበት ካለ የሚታሰብለት ሆኖ በ2 (ሁለት) ዓመት ከ3 (ሦስት)ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ተሻሽሎ ተወስኗል፡፡

## ትዕዛዝ

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ እንዲያዉቁት ለክልሉ ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡እንዲሁም ማረሚያ ቤቱ በዚህ ዉሳኔ መሰረት እንዲያስፈጽም ታጥሮ ታስሮ ለሚገኝበት ማረሚያ ቤት የዉሳኔዉ ግልባጭ ይተላለፍ፡፡ ሲጠይቁ ግልባጩ ለግራ ቀኙም ይሰጣቸዉ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡ መዝገቡ በክረምት በዳኞች እረፍት ጊዜ ተሰርቶ በ8/2/2017 ተነቧል ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ዉሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ. 251772

ቀን ፡- ጥቅምት 07 ቀን 2017 ዓ/ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች፡-ወ/ሮ እመቤት ተመስገን - ጠበቃ አዲሱ ሀረገወይን - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡-1.ረዳት ሳጅን ደስታው አዘነ - በሌሉበት

2. አቶ ንጉሴ ጌትነት - አልቀረቡም

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የባልና ሚስት ንብረት ክርክር የሚመለከት ሲሆን የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በደብረ ማርቆስ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት በተደረገ ክርክር አመልካች ከሳሽ፣ 1ኛ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን የተከራከሩ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ በሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመቃወም አመልካች ሆነው በክርክሩ ተሳትፈዋል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት ባጭሩ፡- ከተጠሪ ጋር የነበረን ጋብቻ የፈረሰ በመሆኑ በጋራ ያፈራናቸው በደብረማርቆስ ከተማ ቀበሌ 10 በተለምዶ ጎተራ እየተባል ከሚጠራው ቦታ ሳተናው ልዩ ሃይል የቤት ሥራ ማህበር አባል በመሆን ተደራጅተን ያገኘነው 150 ካ.ሜ ቦታ ድርሻዬን እንዲያካፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን ተከትሎ በወረዳ ፍርድ ቤት ቦታው የ1ኛ ተጠሪ የግል ሀብት ነው ተብሎ ተወስኗል፡፡ አመልካች ባቀረቡት ይግባኝ መነሻ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቦታው የግራቀኙ የጋራ ሀብት ነው በማለት የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሯል፡፡

2ኛ ተጠሪም በዚህ ውሳኔ መብቴ ተነክቷል በማለት የመቃወም ማመልከቻ አቅርበዋል፤ ይዘቱም ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቦታ እና የመኖሪያ ቤት 1ኛ ተጠሪ በሰጧቸው ውክልና መሰረት ባዶ ቦታ መሸጥ ስለማይቻል በእራሳቸው ወጭ ኮለን በመስራት 1ኛ ተጠሪም በቦታው ላይ መብት ያላቸው ስለመሆኑ የወረዳ ፍርድ ቤት የግላቸው መሆኑን አረጋግጦ የሰጠውን ውሳኔ በማየት ፣ ከእዳና እገዳ ነፃ መሆኑን በማረጋገጥ 1ኛ ተጠሪ ጥር 30/2012 ዓ.ም የሸጡላቸው እንደሆነ፣ በመቀጠልም 1ኛ ተጠሪ ቦታውን ለወ/ሮ ታጫውት ዘለቀ እንዲሸጡ በሰጧት ውክልና መሰረት እንደገና በደብረ ማርቆስ ከተማ አስተዳደር ከተማ ልማት ቤቶች ኮንስትራክሽን አገልግሎት ጽ/ቤት ዘንድ ቀርበው መጋቢት 09/2013 ዓ.ም በተደረገ የሽያጭ ውል በ160,000 (አንድ መቶ ስልሳ ሽህ) ብር በቅን ልቦና ከ1ኛ ተጠሪ ገዝተው በስማቸውም እንዲዞር አድርገው ቤቱንም ኤል ሸፕ በማድረግ በብሎኬት ገንብተው አጠናቀው አሁን ላይ 1.5 ሚሊዮን ብር የሚያወጣ በማድረግ እንደሰሩና ከተለያዩ አበዳሪ የፋይናንስ ተቋማትም በመያዣነት በመስጠት እየኖሩበት የሚገኝ ንብረታቸው መሆኑን በመግለጽ ይግባኝ ሰሚው ችሎት በዚህ ረገድ የሰጠውን ውሳኔ ሽሮ ቤትና ቦታው የ2ኛ ተጠሪ ነው ተብሎ እንዲወሰንላቸው የመቃወም ማመልከቻ አቅርበዋል፡፡

አመልካች 2ኛ ተጠሪ ባቀረቡት የመቃወም ክስ ላይ የሰጡት መልስ ይዘትም በአጭሩ፡- ለክርክሩ መነሻ በሆነው ቤትና ቦታ ላይ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በወረዳ ፍርድ ቤት እና በዚህ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክርክር እያደረጉበት የነበረ መሆኑን የፍርድ ተቃዋሚው 2ኛ ተጠሪም እውቅና የነበራቸው መሆኑን ፣ ይህ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቤትና ቦታው እንዳይሸጥ ወይም እንዳይለወጥ ወይም በማንኛውም ሁኔታ ለ3ኛ ወገን እንዳይተላለፍ የእግድ ትዕዛዝ ሰጥቶ የታገደ መሆኑንም የቦታው ፋይል የሚገኝበትን ቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት ውጤቱን ለዚህ ችሎት የገለፀ በመሆነ መታገዱን የመቃወም አመልካች እውቅና ያላቸው በመሆኑ ቅን ልቦና ገዢ ናቸው ሊባል አይችልም፣ ቦታው ላይ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር እያለን ኮለን የሰራን ሲሆን እስከነኮለኑ 160,000 ብር በሆነ በወረደ ዋጋ 1ኛ ተጠሪ ለፍርድ ተቃዋሚ ቤቱንና ቦታው ሊሸጥ የሚችልበት አግባብ የሌለ በመሆኑ 1ኛ ተጠሪ ለፍርድ ተቃዋሚ አመልካች ቤቱን እና ቦታውን እንዲሸጥ፣ እንዲለውጥ ወይም የአስተዳደራዊ ስራዎችን እንዲፈፅሙ የሰጡት ውክልና ሳይሻር በድጋሜ ለ 3ኛ ወገን ( ወ/ሮ ታጫውት ዘለቀ ) እንዲሸጡ ውክልና የሚሰጥበት አግባብ ባለመኖሩ ስመ ንብረቱ እግድ እያለ ለፍርድ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ተቃዋሚ አመልካች የዞረ ቢሆንም ይህ ሊሆን የቻለበት ምክንያት በተጭበረበረ መንገድ በመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

1ኛ ተጠሪ 2ኛ ተጠሪ ባቀረቡት የመቃወም ክስ ላይ በሰጡት መልስ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት የወረዳ ፍርድ ቤቱ የ1ኛ ተጠሪ የግላቸው መሆኑን አረጋግጦ እንደወሰነ ወዲያው ለ2ኛ ተጠሪ ውክልና በመስጠት የፍርድ ተቃዋሚ አመልካች በእራሳቸው ወጭ ኮለን ከሰሩ በኋላ በድጋሚ ለወ/ሮ ታጫውት ዘለቀ እንዲሸጡ ውክልና በመስጠት በ160,000 ብር ለ2ኛ ተጠሪ በሽያጭ ያስተላለፋላቸው በመሆኑ አመልካች ከሽያጭ ገንዘቡ ላይ በድርሻቸው 80,000 ብር ከሚከፍሏቸው በስተቀር በቤቱ ላይ አሁን መብት የሌላቸው በመሆኑ ይህ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ውሳኔ ተሽሮ ቤትና ቦታው ለፍርድ ተቃዋሚው ተብሎ ቢወሰን ተቃውሞ የለኝም የሚል ነው፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከቀረቡ ማስረጃዎች እና አግባብነት ካለው ህግ ጋር በመመርመር አመልካች ቀደም ሲል እግድ ለዚህ ፍርድ ቤት የጠየቁት በ26/05/2012 ዓ/ም ሲሆን በችሎት ሥራ ላይ የተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ አላገኘንም፣ የቀበሌው አስተዳር ቤቱ መታገዱን የገለጸ ቢሆንም የቤቱ ፋይል የሚገኝበት የደብረ ማርቆስ ከተማ አስተዳደር ከተማ ልማት ቤቶች ኮንስትራክሽን አገልግሎት ጽ/ቤት ምንም እገዳ የሌለበት መሆኑን የገለፀ በመሆኑ፣ አመልካችና 2ኛ ምስክራቸው ሲያስረዱ የፍርድ ተቃዋሚ አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በስር ፍርድ ቤት እና በዚህ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በነበረን ክርክር ይመላለሱ ነበር ይበሉ እንጅ የፍርድ ተቃዋሚ አመልካች በትክክል መቼ ቀን ሲመጣ እንደነበረ ለይተው አላስረዱም፣ የ1ኛ ተጠሪ ውክልና ይዘው ሲከራከሩም የነበረ ስለመሆንም የተረጋገጠ ፍሬ ነገር የለም ፣በአንፃሩ ግን 2ኛ ተጠሪ ጅምር ቤቱን ከ1ኛ ተጠሪ በመጀመሪያው የሽያጭ ውል ጥር 30/2012 ዓ.ም ሲገዙ 1ኛ ተጠሪ ቦታው የግላቸው መሆኑ በስር ፍርድ ቤት የተወሰነ መሆኑ እና በቦታው ላይ እግድ የሌለበት መሆኑን አረጋግጠው ቦታው ላይ መብት ካለው ከ1ኛ ተጠሪ ላይ መዋለ ንዋይ በማፍሰስ ቤቱን ኤል ሽፕ የብሎኬት ግንባታ በመገንባት አጠናቀው ጨርስው በስማቸው አዙረው እና ካርታ አሰርተው ቤቱንም በመያዣ አስይዘው ከኦሮሚያ ኢንተርናሽናል ባንክ እና ፒስ ማይክሮ ፋይናንስ በድምሩ 900,000 ሺ ብር ተበድረውበት የሚገኙ ስለመሆኑ በተሻለ መንገድ በሰው እና በሰነድ ማስረጃ ያስረዱ በመሆኑ 2ኛ ተጠሪ ቤቱን ሲገዙ ቦታው ክርክር ያለበት መሆኑን አውቀት ነበራቸው የሚያስብል አይደለም ፡፡በመሰረቱ ቅን ልቦናን መሰረት በማድረግ የማይንቀሳቀስ ንብረትን የገዛ ሰው በፍ/ብ/ህ/ቁ 1816 ፤ ፍ/ብ/ህ/ቁ 2882-2884 ድንጋጌዎች ይዘት እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ በሰ/መ/ቁ 23331፣28663፣41116 እና መብት ሊጠበቅላቸው እንደሚገባ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበት የሚገኝ በመሆኑ እና 1ኛ ተጠሪ ለ2ኛ ተጠሪ ጥር 30/2012 ዓም ጀምሮ የሸጡለት በመሆኑ እንዲሁም አመልካች ይህን ውል እና ከዚያ በኋላ የተደረገውን የሽያጭ ውል ህጋዊ ስርዓቱን ተከትለው ስላላስፈረሱ 2ኛ ተጠሪ አከራካሪውን ጅምር ቤት እንደነበረ በቅን ልቦና መብት ካለው 1ኛ ተጠሪ ገዝተው የያዙ መሆናቸው የተረጋገጠ በመሆኑ እንዲሁም

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ከሚመለከተው የመንግስት አስተዳደር በህጉ መሰረት በስሙ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ተስርቶ የተሰጠው ሰው ደግሞ የማይንቀሳቀሰው ንብረት ባለቤት ሆኖ እንደሚገመት በህጉ የተመለከተ በመሆኑ 2ኛ ተጠሪ አከራካሪው ቤት የተሰራበትን ባዶ ቦታ እና ከዚሁ ቦታ ላይ የተሰራው ቤት የ2ኛ ተጠሪ ሃብት ነው በማለት ቀድሞ የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ለክርክሩ መነሻ የሆነው የቤት መስሪያ ባዶ ቦታ የአመልካና የ1ኛ ተጠሪ የጋራ ንብረት የነበረ በመሆኑ 2ኛ ተጠሪ ከ1ኛ ተጠሪ ውክልና ወስደው በእራሳቸው ወጭ መሰረት እና ኮለን በመገንባት በ 160,000 ብር 2ኛ ተጠሪ የሸጡላቸው መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 34(1) ፣ በአብክመ የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 73(1) እና (2) ፣ ከ 101 እስከ 103 እንደተመለከተው ባልና ሚስት በትዳር በነበሩበት ወቅት በጋራ ያፈሩት ወይም በግብይት ያገኙት ገንዘብ የግል ተብሎ በሚመለከተው አካል እስካልተመዘገበ ድረስ የጋራ ንብረት እንደሆነ እና በፍች ጊዜ ባልና ሚስቱ እኩል የመካፈል መብት ያላቸው ስለመሆኑ ተደንግጎ የሚገኝ በመሆኑ ምንም እንኳ ቤቱ እስከተሸጠበት ድረስ የተከናወነውን ግንባታ አመልካችና 1ኛ ተጠሪ አስተዋፅዖ ያላደረጉበት ቢሆንም እስከሚሸጥ ድረስ ግን የጋራ ንብረት እንደነበር ተደርጎ የሚወሰድ በመሆኑ 1ኛ ተጠሪ ካገኘው የሽያጭ ገንዘብ 160,000 ላይ ግማሹን ማለትም 80,000 ለአመልካች ሊከፍል ይገባል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ይህንን ውሳኔ በመቃወም በየደረጃው ላሉ ፍርድ ቤቶች ቅሬታ ቢያቀርቡም ውሳኔው ሳይቀየር ቀርቷል፡፡

አመልካች ነሀሴ 1 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይህን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ሲሆን ይዘቱም፡- አመልካች ቦታው ለ 2ኛ ተጠሪ ከመሸጡ በፊት በፍርድ ቤት እግድ አቤቱታ አቅርቤ ያሳገድኩ ቢሆንም የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የእግዱ ውጤት ከመዝገቡ ጋር የተያያዘው ችሎቱ ተሰይሞ ስለመሆኑ መዝገቡ አያስረዳም በሚል እግዱ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 154 እና 156(1) ያለውን ውጤት ቀሪ በማድረግ የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ ማስረጃዎችን በተገቢው መንገድ ሳይመረምሩ የሰጡት ውሳኔ ነው፣2ኛ ተጠሪ ጥር 30 ቀን 2012 ዓ.ም የመጀመሪያ ሽያጭ ውል እንደተደረገ ተረጋግጦ እያለ እና ይሄም 2ኛ ተጠሪ የቅን ልቦና ገዥ አለመሆናቸውን የሚጠቁም ሆኖ ሳለ በተጭበረበረ ሁኔታ የእግድ ትዕዛዙ ወጥቶ እግድ እንደሌለ አስመስሎ በድጋሚ መጋቢት 09 ቀን 2013 ዓ.ም የሽያጭ ውል ተደርጎ ስም ዝውውር መካሄዱ ብቻ 2ኛ ተጠሪን ቅን ልቦና ገዥ አያደርጋቸውም፣ፍርድ ቤቱ የሰጠው እግድ ትዕዛዝ እንዴት እንዳልተፈጸመ አጣርቶ መወሰን ሲገባው የእግዱ ውጤት ከመዝገቡ ጋር የተያያዘው ችሎቱ ተሰይሞ አይደለም በሚል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፣በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የሰበር ሰሚው ችሎትም የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ውሳኔውን ያስተላለፈው የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አከራካሪውን ቤት በተመለከተ 2ኛ ተጠሪ የቅን ልቡና ገዢ ናቸው በማለት የአመልካችን ክርክር ውድቅ በማደረግ የወሰነው በተለይም የክፍሉ ቀበሌ አስተዳደር ፅ/ቤት በ 19/07/2012

ዓ.ም በተጻፈ ሰጥቷል በተባለው ምላሽ እግዱን ተቀብሎ የማህደሩ አካል ማድረጉን የገለፀበት ከመሆኑ አንፃር በርግጥም የእግዱ ትዕዛዝ በቀበሌው ማህደር ውስጥ የሚገኝ መሆን አለመሆኑን፣ የእግድ ትዕዛዝም መሰጠት አለመሰጠቱን በቀበሌው ማህደር ውስጥ የሚገኝ ከሆነስ የቤቱ ዝውውር እንዴትና በምን አግባብ እንደተፈፀመ እና የመሳሰሉትን አጣርቶ ነውን የሚለውን ለመመርመር ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ታዟል፡፡

1ኛ ተጠሪ በቀረበው የሰበር አቤቱታ ላይ መልስ እንዲቀርቡ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥሪ ተደርጎላቸው መልስ ስላላቀረቡ መልስ የማቅረብ መብታቸው ታልፏል፡፡ 2ኛ ተጠሪ ሚያዝያ 8 ቀን 2016 ዓ.ም የሰጡት መልስ ይዘት፡- በአከራካሪው ቤትና ቦታ ላይ የከፍተኛ ፍርድ ቤቱ የሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ይህ የማይንቀሳቀስ ንብረት ተመዝግቦ በሚገኝበት የደ/ማርቆስ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማት ኮንስትራክሽን አገልግሎት ጽ/ቤት ወይም ደግሞ በተለምዶ ማዘጋጃ በሚባለው አካል የእግድ ትዕዛዝ ከፋይሉ ላይ የሌለ ስለመሆኑ ተረጋግጦ ስመ ንብረት ዞሮልኛል ፡፡ በቀበሌ አስተዳደር የቤቱ ማሕደር የማይገኝ በመሆኑ እግድ ሊመዘግብ አይችልም፡፡ ይህም አንድ ጠንቃቃ ገዥ ሊፈፅመው የሚገባውን ተግባር በአግባቡ ማከናወኔን የሚያሳይ ነው፡፡ 1ኛ ተጠሪ ከአመልካች ጋር ፍቺ የፈፀመ መሆኑንና ጅምር ኮለን የወጣበት ቦታ የግሉ ተብሎ ውሳኔ የተሰጠለት መሆኑን የፍርድ ቤቱን ውሳኔ በማየት አረጋግጬ ጥር 30 ቀን 2012 ዓ.ም ግዥ ከፈፀምሁ በኋላ የቤቱን መሰረታዊ ነገሮች አሟልቼ የሰራሁት 2ኛ ተጠሪ ነኝ፣ ከዚህም በተጨማሪ ይህንን የማይንቀሳቀስ ንብረት ራሴው ሰርቼ ከጨረስሁ በኋላ ከተለያዩ የፋይናንስ ተቋማት ይህንን የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ በማድረግ ቤትና ቦታው እንዲታገድ ተደርጎ 700,000 ብር (ሰባት መቶ ሺ) ብር ብድርም ተበድሬበት እገኛለሁ፣ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ 220119፣ 23331 ፣ 28663 ፣ 41116 እና በሌሎች በርካታ መዝገቦች የቅን ልቦና ገዥዎች መብት ሊጠበቅላቸው እንደሚገባ የሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም በመመልከት በዚህ ጉዳይ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡ አመልካች በሰጡት የመልስ መልስ ቀደም ሲል የቤቱ ማሕደር የነበረው በቀበሌ አስተዳደር በመሆኑ እግዱን መመዝገቡ ተገቢ ነው በማለት የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ህጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

እንደመረመርነው አመልካችና 1ኛ ተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍቺ ከፈረሰ በኋላ የንብረት ክፍፍል ክርክር ያደረጉ ሲሆን በደብረማርቆስ ከተማ ቀበሌ 10 የሚገኝ 150 ካሬ ሜትር ቦታ የጋራ ንብረት ስለሆነ እኩል እንዲካፈሉ በሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በቀን 24/06/2013 ዓ/ም ተወስኗል፡፡ 2ኛ ተጠሪ ውሳኔው መብቴን ነክቷል በሚል በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት የመቃወም ማመልከቻ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም ንብረቱን ከ1ኛ ተጠሪ በቀን 30/05/2012 ዓ/ም ከዕዳና እገዳ ነጻ መሆኑን በማረጋገጥ ገዝቼ ቤቱን

በመገንባት በቀን 09/07/2013 ዓ/ም በጽ/ቤት በተደረገ ውል ንብረቱ ተላልፎልኛል የሚል ነው፡፡ ክርክሩን በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሰረት መምራት እና መቆጣጠር የፍርድ ቤቱ ኃላፊነት ሲሆን በተገቢው ሁኔታ ካልተመራ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ዓላማዎች የሆኑትን እንደ አንጻራዊ እውነትን የመፈለግ፣ ሥነ-ሥርዓታዊ ፍትህ፣ ክርክርን ውጤታማ፣ ወጭና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ መምራት የመሳሰሉትን ማሳካት ስለማይቻል የተከራካሪዎችን መብት ይነካል፡፡ ክርክር የሚወሰነው በተጠየቀው ዳኝነት አግባብ እንደሆነ የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 182(2) ላይ ተመልክቷል፡፡ ፍርድ ቤቱም ከቀረበው ዳኝነት አኳያ ከግራቀኙ ክርክር በመነሳት በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 246 እና ተከታዮቹ መሠረት በተነሱት ጉዳዮች ጭብጥ መስርቶ ውሳኔ የመስጠት ኃላፊነት አለበት፡፡

ግራቀኙን ያከራከረው የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት ቤቱ እንዳይሸጥ የታገደ ስለመሆኑ የገለጸ ቢሆንም ከፍርድ ቤቱ የችሎት ሥራ እግድ የተሰጠ ስለመሆኑ መዝገቡ አያሳይም፡፡ 2ኛ ተጠሪ ንብረቱ ላይ እግድ የሌለ መሆኑን በማረጋገጥ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል ሥርዓቱን ጠብቀው የፈጸሙት ውል በመሆኑ እና ንብረቱም በ2ኛ ተጠሪ ሥም ተላልፎና ተመዝግቦ ስለሚገኝ ቤቱ የ2ኛ ተጠሪ ንብረት ነው፡፡ 1ኛ ተጠሪ ከሽያጩ ገንዘብ ግማሹን ብር 80,000.00 ለአመልካች ይክፈሉ በማለት አስቀድሞ የሰጠውን ፍርድ አሻሽሏል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝና በሰበር የተመለከቱት የአማራ ክልል ፍርድ ቤቶች ውሳኔውን አጽንተዋል፡፡

የአመልካች አንደኛው መከራከሪያ የሥር ወረዳ ፍርድ ቤት ንብረቱ የ1ኛ ተጠሪ የግል ንብረት ነው በማለት በሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት እንደቀረበ እግድ ተሰጥቷል የሚል ነው፡፡ እግዱ ተሰጥቶ የነበረው ንብረቱ ላይ ክስ በመቅረቡ የተነሳ ነው፡፡ እግድ በሠው የንብረት መብት አጠቃቀም ላይ ገደብ የሚፈጥር ነው፡፡ በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 40(1) ላይ ጥበቃ የተደረገለት ንብረት መብት ላይ ገደብ ለማድረግ ደግሞ በሕግ በግልጽ በተመለከተ፣ ውስን ጉዳይና አፈጻጸሙም መብቱን መልሶ የመውሰድ ያህል ውጤት በማይፈጥር ሁኔታ ውስጥ ብቻ ሊሆን ይገባል የሚለው ስለሠብዓዊ መብት ጥበቃ የተደረገ የሥምምነት ድንጋጌዎች ሆነ በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ የተቀረጸ የሕግ መርሕ ነው፡፡ በፍትሐብሔር ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 154 እና 155 መሠረት የሚሰጥ እግድ፣ የፍትሐብሔር ጉዳዮችን በማየት ላይ ያለ አንድ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ፍርድ ከመስጠቱ በፊት ከሚሰጣቸዉ የተለያዩ ጊዜያዊ የእግድ ትዕዛዞች አንዱ ነዉ (የህጉ አንቀጽ 147-159 ይመለከቷል)፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 154 ላይ እና በተከታዩ አንቀጽ 155 ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለዉ ክርክሩ በማናቸዉም ደረጃ ላይ ባለበት ጊዜ ሌላዉን ተከራካሪ ወገን ሊጎዳ የሚችል አንድ የተወሰነ ተግባር እንዳይፈጸም በፍርድ ቤት የሚሰጥ ትዕዛዝ ነዉ፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች መሠረት እግድ የሚሰጠዉ አንደኛ በንብረቱ ላይ የሚፈጸመዉ ተግባር ሌላዉን ተከራካሪ የሚጎዳ ሲሆን (አንቀጽ 154)፣ ሁለተኛ ክርክሩ ከዉል ጋር የተያያዘ እንደሆነ ዉል

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

እንዳይፈርስ ወይም አንድ ተግባር እንዳይፈጸም የሚያሰጋ ሆኖ ሲገኝ (አንቀጽ 155) ስለመሆኑ ከየድንጋጌዎቹ ይዘት የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡

የሥር ፍርድ ቤት መከራከሪያውን ያለፈው እግድ እንዲሰጥ ጥያቄ የቀረበ ቢሆንም እግድ መሰጠቱን መዝገቡ ላይ ያለው የችሎት ሥራ አያሳይም የሚል ነው፤ በሌላ በኩል የክፍሉ ቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት ንብረቱ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ መታገዱን ገልጿል፣ ለእግዱ ምክንያት የሆነው ትዕዛዝ ከፍርድ ቤት የወጣ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር የቀበሌው አስተዳደር ጽ/ቤት የደረሰውን የእግድ ትዕዛዝ እንዲልክ በማድረግ ማረጋገጥ ይቻል ነበር፤ እግድ እንዲሰጥ የጠየቀ ተከራካሪ ከፍርድ ቤቱ የእግድ ትዕዛዝ ወጪ በማድረግ ወስዶ ለሚመለከተው አካል ካደረሰ የትዕዛዙ ውጤት ተጠቃሚ ሊሆን ይገባል፡፡ በትክክልም የእግድ ትዕዛዙ ከፍርድ ቤት ወጪ የተደረገ ስለመሆኑ ከቀበሌ አስተዳደር የተላከውን ትዕዛዝ በመመልከት ውጤን መወሰን ሲገባ መዝገቡ ላይ የእግድ ትዕዛዝ የለም በማለት የሥር ፍርድ ቤት ክርክሩን ማለፉ ስህተት ያለበት ነው፡፡ 2ኛ ተጠሪ በዚህ ችሎት ባቀረቡት ክርክር በቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት የማንቀሳቀስ ንብረት ማሕደር የማይገኝ በመሆኑ የእግድ ትዕዛዝ ለቀበሌው ቢደርስ እንኳን ሕጋዊ ውጤት የለውም ብለዋል፡፡ አመልካች በበኩላቸው በጊዜው በነበረ አሠራር የማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ የሚገኘው በቀበሌ አስተዳደር ነው በማለት የሚከራከሩ በመሆኑ እግዱ ተሰጠ በተባለበት በ2012 ዓ/ም በከተማው የነበረው አሠራር በማጣራት አብሮ ሊመረመር የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በሌላ በኩል ከክርክሩ የተገነዘብነው ክርክር ያስነሳው ንብረት የአመልካች እና የ1ኛ ተጠሪ የጋራ ንብረት ነው ተብሎ የተወሰነው በየካቲት 24 ቀን 2013 ዓ/ም ነው፡፡ 2ኛ ተጠሪ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ጥር 30 ቀን 2012 ዓ/ም እና መጋቢት 09 ቀን 2013 ዓ/ም የሽያጭ ውል ማድረጋቸውን ከክርክራቸው መረዳት ይቻላል፡፡ ውል ሊመሠረት የሚገባው ችሎታ ባላቸው፣ በተዋዋዮች ነጻ ፈቃድ፣ የሚቻልና ሕጋዊ በሆነ ዓላማና ጉዳይ ላይ በሕግ የተመለከተውን የውል አጻጻፍ ፎርም ተከትሎ ሊሆን እንደሚገባ በፍ/ሕ/ቁ. 1678 ላይ ተመልክቷል፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ በግዥ የባለቤትነትን መብት ለማግኘት ግዥ ሲፈጽሙ አንድ ጠንቃቃ ገዥ በሕግም ሆነ በአሠራር ሊያደርገው የሚገባውን ጥንቃቄ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ሕግ የተለየ ጥበቃ ስለሚያደርግ የሀብትነት ሠነድ ስለሚወጣበት፤ ሠነዱ ስለሚገኝበት የሥራ ክፍል፣ ውሉ ስለሚፈጸምበት እና ንብረቱ ስለሚተላለፍበት ሥርዓት የተገለጸውን የመከተል ግዴታ ይጥላል፡፡ ሽያጭ ውል ሊፈጸምበት በሚችል የከተማ ክልል ውስጥ ያለ፣ ቦታው ላይ ቤት ያረፈበትና ስለቤቱ የሚመለከቱ ሠነዶች በቤቱ ባለሀብት ሥም በማይንቀሳቀስ ሀብት ምዝገባ ክፍል መገኘቱ፣ ውሉ በፍ/ሕ/ቁ. 1723(1) በተመለከተው አግባብ በውል አዋዋይ ፊት መደረግና እና በሦስተኛ ወገን ላይ ውጤት እንዲኖረው ደግሞ በፍ/ሕ/ቁ. 2878 አግባብ በማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ የተመዘገበ መሆን እንደሚኖርበት ሰበር ችሎቱ በመዝገብ ቁጥር 222099 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት ላይ አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

2ኛ ተጠሪ ካደረጓቸው ውሎች አንጻር፤ አመልካች ላይ ውጤት የሚኖረው በማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ የተመዘገበው ውል በመሆኑ፤ በውል አዋዋይ ፊት ተደርጎ የተመዘገበው ውል የትኛው ነው፣ 2ኛ ተጠሪ ንብረቱ የአመልካችና የ1ኛ ተጠሪ የጋራ ንብረት ነው ተብሎ ከመወሰኑ በፊት በንብረቱ ላይ ሕጋዊ ባለመብት ሆነዋል ወይስ አልሆኑም፣ ውሉ የተመዘገበው አመልካች በፍርድ ባለመብት ከሆኑ በኋላ ከሆነ 2ኛ ተጠሪ ከፍርድ በኋላ ያገኙትን መብት መሠረት በማድረግ አስቀድሞ የተሰጠን ፍርድ ለመቃወም መብት ያላቸው መሆን አለመሆኑንና ንብረቱ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ነው ተብሎ ከተወሰነ በኋላ የተገኘ መብት በፍርዱ ላይ የሚኖረው ውጤት በጭብጥነት ተይዞ ሊመረመር የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፤ ይሕ ሳይከናወን ንብረቱ የ2ኛ ተጠሪ ነው በሚል የተደረሰበት መደምደሚያ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ውሳኔ

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 120015 ግንቦት 01 ቀን 2015 ዓ/ም፣ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 01-59207 ሕዳር 27 ቀን 2015 ዓ/ም እና የምሥራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 0145295 ግንቦት 26 ቀን 2014 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1)(ለ) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የምሥራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውሳኔ የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ 2ኛ ተጠሪ በሕግ አግባብ ውል ያደረጉት ንብረቱ የአመልካችና የ1ኛ ተጠሪ የጋራ ንብረት ነው ተብሎ ከመወሰኑ በፊት ወይስ በኋላ መሆኑና የዚህን ሕጋዊ ውጤት በፍርዱ በተመለከተው አግባብ እንዲመረምር፣ በንብረቱ ላይ ከፍርድ ቤት ወጪ የተደረገ የእግድ ትዕዛዝ መኖር አለመኖሩን ከቀበሌው አስተዳደር በመመልከት፣ ቀበሌው በጊዜው በነበረው አሠራር የማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ የሚይዝና እግድ የሚቀበል መሆኑን አለመሆኑን በማጣራት እና ግራቀኙ በጉዳዩ ላይ ክርክር ካደረጉበት በኋላ ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች በመነሳት ሕጋዊ ውጤቱን እንዲወሰን ጉዳዩን በሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/2/ መሠረት መልሠናል፡፡

3. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡ የምሥራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውሳኔው መሠረት እንዲፈጽም አዘናል፡፡ ይጻፍ
- በዚህ ችሎት ሰኔ 05 ቀን 2016 ዓ/ም የተሠጠው እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁጥር 251952

ጥቅምት 07 ቀን 2017 ዓ/ም

ዳኞች፡-እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች፡- አቶ ደስታ ኤሬሶ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አልማዝ አበቲ አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ በዳኞች የእረፍት ጊዜ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች በቀን 05/12/2016 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የነገሌ አርሲ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 44427 በቀን 08/06/2015 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 46140 በቀን 10/09/2015 ዓ.ም ካሻሻለው በኋላ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 408508 በቀን 24/09/2015 ዓ.ም እንዲሁም የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 424386 በቀን 08/10/2015 ዓ.ም በማጽናት መወሰናቸው መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት የተፈጸመበት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለታቸው ሲሆን በስር ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ከሳሽ ሆነው ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ሆነው በባልና ሚስት ንብረት ክፍፍል ጉዳይ ተከራክረዋል፡፡

በስር ፍ/ቤት አመልካች በቀን 28/06/2014 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት ክስ ከተጠሪ ጋር ያላቸው ጋብቻ እንዲፈርስና የጋራ ናቸው ያሏቸውን ተንቀሳቃሽ ንብረቶችን በመዘርዘር እንድንካፈል ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪም በቀን 08/07/2014 ዓ.ም ከዚያም በቀን 07/11/2014 ዓ.ም አሻሽለው ጽፈው ባቀረቡት መልስና የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በነገሌ አርሲ ወረዳ መጃ ቀበሌ ውስጥ የሚገኝ አዋሳኙ በክሱ የተመለከተው በ3700 ካ.ሜ ቦታ ላይ ያረፈ በአመልካች ስም ተመዝግቦ የሚገኝ 180 ሉክ ቆርቆሮ መኖሪያ ቤት፣ ሁለት ጥማድ የእርሻ መሬት እንዲሁም ተንቀሳቃሽ የቤት እቃዎችን ዘርዝረው አመልካች ያካፍለኝ በማለት የጠየቁ ሲሆን አመልካች በክሳቸው ከዘረዘራቸው ተንቀሳቃሽ ንብረቶች ውስጥ የተወሰኑትን በማመን መልስ አቅርበዋል፡፡

አመልካችም ለተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ ባቀረቡት መልስ ተጠሪ በ3700 ካ.ሜ ቦታ ላይ ያረፈ ቤት ብለው ካቀረቡት ውስጥ በአጠቃላይ በ105 ሉክ ቆርቆሮ የተሰራው ቤት አባቴ ከተጠሪ ጋር ከመጋባቴ በፊት በስጦታ የሰጠኝና በተለያየ ጊዜ የሰራሁት እና በስሜ የተመዘገበ የግል ንብረቴ ነው፡፡ የእርሻ መሬቱም ስፋቱ 0.415 ሔክታር ወይም 1 ጥማድ ሆኖ ትንሽ የሚተርፍ መሬት ያለው ሲሆን ይህንንም አባቴ በስጦታ የሰጠኝና በስሜ የተመዘገበ የግል ንብረቴ በመሆኑ ተጠሪ ሊካፈሉ አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡

በስር ፍ/ቤት ከ1ኛ እስከ 3ኛ የተዘረዘሩት ጣልቃ ገቦችም አመልካችና ተጠሪ ከሚከራከሩባቸው ንብረቶች ውስጥ የኔ ንብረት ነውና ከክርክሩ ይውጣልኝ የሚሉትን ንብረት ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ግራ ቀኙ ጋብቻ ከመፈጸማቸው በፊት ክስ ከቀረበበት 3700 ካ.ሜ ውስጥ አመልካች 1000 ካ.ሜ በሚሆነው ቦታ ላይ አባቱ በስጦታ ሰጥተውት በተለያየ ጊዜ ቤት የሰራ መሆኑን እና ስጦታውም ስልጣን ባለው አካል ተመዝግቦ የሚገኝ ስለመሆኑ ምስክሮችና ከአርሲ ነገሌ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት የቀረበው ማስረጃ የሚያስረዳ ሲሆን የቀረው ቦታ ደግሞ በአመልካች እጅ የሌለና በ1ኛ የስር ጣልቃ ገብ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ስለመሆኑ በምስክሮች የተረጋገጠ በመሆኑ አመልካችና ተጠሪ በክሱ በተመለከተው ቦታ ላይ በጋራ ያፈሩት ቤት የለም፡፡ የእርሻ መሬቱን በተመለከተም የአመልካች አባት ለአመልካች በሰርጉ እለት በስጦታ የሰጡት ሥለመሆኑ የተመሰከረ ሲሆን ከአካባቢው መሬት አስተዳደር የቀረበው ማስረጃም ስጦታው የተመዘገበ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ስጦታው በ2011 ዓ.ም ተደርጎ ይህ ክስ የተመሰረተው በ2014 ዓ.ም በመሆኑ መሬቱን በመንከባከብ እና በመጠቀም የረዥም ጊዜ ተሳትፎ የሌለ በመሆኑ የጋራ ነው ሊባል

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አይችልም፡፡ ተንቀሳቃሽ ንብረቶችን በተመለከተ በማስረጃ የተደገፉ ባለመሆናቸው ታልፈዋል፡፡ ልጅ ቀለብ በወር ብር 800 አመልካች ለተጠሪ ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪም በዚህ ውሳኔ ቅሬታ አድሮብኛል በማለት ለምእራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን የእርሻ መሬቱን በተመለከተ መሬቱ በአመልካች ስም ተመዝግቦ ያለና ከተጠሪ ጋር በጋራ የሚጠቀሙበት መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑና የእርሻ መሬት ይዞታን በተመለከተ አንድ አርሶ አደር ያለው መብት የመጠቀም መብት ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.130/1999 የሚያስረዳ በመሆኑ ተጠሪ በዚህ መሬት ላይ መብት ያላት መሆኑን የሚያረጋግጥ ሆኖ እያለ የስር ፍ/ቤት ባለ መብት አይደለችም ማለቱ ስህተት ያለበት በመሆኑ ይኸው መሬት የጋራ ነው አመልካችና ተጠሪ እኩል ይካፈሉ፡፡ ተንቀሳቃሽ ንብረቶችን እና የልጅ ቀለብን በተመለከተ የተሰጠው ውሳኔ በምክንያት እና በተገቢው ማስረጃ የተደገፈ ባለመሆኑ አስፈላጊውን ማስረጃ በማስቀረብ አጣርቶ እንዲወስን ጉዳዩ ለስር ፍ/ቤት ይመለስለት በማለት የስር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡

አመልካችም በዚህ ውሳኔ ቅሬታ አድሮብኛል በማለት በመጀመሪያ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት የደቡብ ምድብ ይግባኝ ሰሚ ችሎት በኋላም ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ ቢያቀርቡም ፍ/ቤቶቹ ጉዳዩን መርምረው የምእራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ስህተት የለበትም በማለት አቤቱታውን ውድቅ አድርገዋል፡፡

አመልካችም የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት በ05/12/2015 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ለዚህ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፦ ለዚህ ክርክር ምክንያት የሆነው ስፋቱ 0.415 ሔክታር የሆነው የእርሻ መሬት ከተጠሪ ጋር ከመጋባታችን በፊት ወላጆቼ በስጦታ የሰጡኝና ስጦታውም ስልጣን ባለው አካል ተቀባይነት አግኝቶ የተመዘገበ የግል ንብረቴ ሲሆን የኦሮሚያ ክልል የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 73 ባልና ሚስት ጋብቻ ከመመስረታቸው በፊት ያላቸው ንብረት የግል ሆኖ እንደሚቀር እንዲሁም በአንቀጽ 113 (1) ባልና ሚስት ንብረታቸው የግል ስለመሆኑ በማስረዳት መልሰው መውሰድ የሚችሉ ስለመሆኑ የሚደነግግ ሆኖ ባለበት ሁኔታ የስር ፍ/ቤት ለጉዳዩ አወሳሰን ተገቢነት የሌለውን የገጠር መሬት አስተዳዳር አዋጅን መሰረት አድርጎ ይኸው መሬት የጋራ ነው በማለት መወሰኑና ሳይታረም መታለፉ፤ የጋብቻ ግንኙነቱ ጸንቶ የቆየው ለ3 አመታት ብቻ በመሆኑ ለዘመናት የተፈራን ንብረት ተጠሪ ይካፈሉ ተብሎ መወሰኑ ፍትሃዊነት የጎደለው መሆኑ፤ የገጠር መሬት መተላለፍ ያለበት ለአርሶ አደር እንደሆነ ህጉ የሚደነግግ ሲሆን ተጠሪ ቋሚ ገቢ ያላቸው የመንግስት ሰራተኛ ከመሆናቸው ባሻገር መሬቱ ለ2 ይካፈል ቢባል የሚቀረው በጣም ጥቂት ስለሚሆንና አመልካችም ሌላ መተዳደሪያ የሌለኝ በመሆኑ ተጎጂ የሚያደርገኝ ሲሆን በአንጻሩ ተጠሪን ከሚያገኙት ደሞዝ በተጨማሪ ተጠቃሚ የሚያደርግ በመሆኑ ይካፈሉ መባሉ ፍትሃዊነት የጎደለውና መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ የነገሌ አርሲ ወረዳ

ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ጸንቶ ከዚያ በላይ በየደረጃው ያሉት የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ እንዲሻርልኝ ስል እጠይቃለሁ የሚል ነው፡፡

አቤቱታው የቀረበለት የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ለዚህ ችሎት ከመራው በኋላ ይህ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ፡- የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በእርሻ መሬት ይዞታ ላይ አርሶ አደር ያለው መብት የመጠቀም መብት ነው፤ አመልካችና ተጠሪ አካራካሪ የሆነውን 0.415 ሄክታር የእርሻ መሬት በጋራ ሲጠቀሙበት የቆዩ በመሆኑ መሬቱ የአመልካችና የተጠሪ የጋራ ሃብት ነው እኩል ይካፈሉት በማለት መወሰኑና ይህም ውሳኔ በየደረጃው ባሉ የክልሉ ፍ/ቤቶች የመጽናቱን አግባብነት ከኦሮሚያ ክልል የገጠር መሬት አጠቃቀም እና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 130/1999፣ ደንብ ቁጥር 151/2005 እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 247389 ከሰጠው ውሳኔ ጋር በማገናዘብ ሊመረመር የሚገባው ሆኖ ስለተገኘ ተጠሪዎች መልስ ይስጡበት በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪም በጋዜጣ ተጠርተው መልስ ያላቀረቡ በመሆኑ መልስ የማቅረብ መብታቸው ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለፀውን ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ፣ ከጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እና ቅሬታው ለሰበር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ነጥብ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተው መርምሮታል፡፡በመሰረቱ ባልና ሚስት ጋብቻቸውን በሚፈፅሙበት ጊዜ በየግል የነበሯቸው ንብረቶች ወይም ከጋብቻ በኋላ በውርስ ወይም በስጦታ በየግላቸው ያገኟቸው ንብረቶች የግል ንብረቶቻቸው ሆነው እንደሚቀሩ፣ በአንፃሩ ግን በጋብቻው ወቅት ከግል ጥረታቸውና ከግል ወይም ከጋራ ንብረታቸው የሚያገኟቸው ገቢዎችና ውጤቶች ሁሉ ደግሞ የጋራ ሀብቶቻቸው እንደሚሆኑ የተሻሻለው የኦሮሚያ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁ/83/1996 በአንቀፅ 73 እና 78 /1/ ያመለክታል፡፡አሁን በያዝነው ጉዳይ ጉዳዩን በመጀመሪያ የዳኝነት ስልጣኑ የተመለከተው የነጌሌ አርሲ ወረዳ ፍርድ ቤት አከራካሪውን 0.415 ሄክታር የእርሻ መሬት የአመልካች የግል ሀብት ነው በማለት የደመደመው በዋነኝነት ሁለት ምክንያቶችን በመጥቀስ ነው፡፡ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን ምስክሮች በመስማትና ከተገቢው የአስተዳደር አካል በማጣራት የአመልካች ምስክሮች በአከራካሪው የእርሻ መሬት ከግራ ቀኙ ጋብቻ በፊት ሲጠቀሙበት የነበረው የአመልካች አባት መሆናቸውን ሲያስረዱ ከመሬት አስተዳደር የቀረበው ምላሽ አከራካሪውን የእርሻ መሬት አመልካች ከአባታቸው በስጦታ ያገኙት መሆኑን ማረጋገጡን የመጀመሪያ ምክንያት አድርጎ ያስቀመጠ ሲሆን የግራ ቀኙ ጋብቻ ከሚያዚያ 2011 ዓም እስከ 2014 ዓም ብቻ የቆየ መሆኑ በመሬቱ መጠቀም ላይ ተጠሪ የረዥም ጊዜ ተሳትፎ የሌላቸው መሆኑን የሚያሳይ መሆኑን ፍርድ ቤቱ አከራካሪው የእርሻ መሬት የአመልካች የግል ሀብት ነው ለሚለው መደምደሚያው በሁለተኛ ምክንያትነት መጠቀሙን የስር ፍርድ ቤት መዝገብ ያሳያል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በመሰረቱ ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠን ውሳኔ የመሻርና የማሻሻል ስልጣን ያለው ቢሆንም በዚህ አግባብ ውሳኔውን ሲሰጥ ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎች ከተገቢው ህግ ጋር በመመርመር ተገቢ ነው የሚለውን ምክንያቱን በዝርዝር ማስቀመጡ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡አሁን በያዝነው ጉዳይ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አከራካሪው የእርሻ መሬት የግራ ቀኙ የጋራ ሀብት ነው በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ከዚህ ነጥብ አንፃር በመሻር የወሰነው በመሬቱ ግራ ቀኙ ሲጠቀሙ መቆየታቸውን ፤በእርሻ መሬት ላይ ያለው መብት ከመነሻውም የመጠቀም መብት መሆኑን በመጥቀስ ቢሆንም በስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙ ክርክር በተመረመረበት አግባብ የግራ ቀኙ ጋብቻ ለሶስት አመት ያህል ብቻ የቆየ መሆኑን በማመዛዘን በመሬቱ የመጠቀም የረዥም ጊዜ ተሳትፎ ያላቸው መሆን አለመሆኑን መመርመሩን የስር ፍርድ ቤት መዝገብ አያሳይም፡፡ከዚህም በተጨማሪ የስር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ በአስተዳደር አካሉ ከተረጋገጠው የስጦታ ውል አንፃር የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሳይመረምር የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ መሻሩ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በዝርዝር በመመርመርና በመተቸት ተገቢ ነው የሚለውን ምክንያት ሳያስቀምጥ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ የሻረ መሆኑን ስለሚያሳይ ጉዳዩን በየደረጃው የተመለከቱት ፍርድ ቤቶችም ይህንን በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተፈፀመን መሰረታዊ የህግ ስህተት ሊያርሙ ሲገባ ማፅናታቸው በመደምደሚያቸው መሰረታዊ የህግ መፈፀማቸውን ስለሚያሳይ፤በአጠቃላይ የነጌሌ አርሲ ወረዳ ፍርድ ቤት ማስረጃን የመስማት፤የመመርመርና የመመዘን ስልጣኑን በመጠቀም የግራ ቀኙን ማስረጃዎች በመስማት እና ተገቢውን ማጣራት በማድረግ አከራካሪውን የእርሻ መሬት አመልካች ከአባታቸው በስጦታ ያገኙት መሆኑን ማረጋገጡን እንዲሁም የግራ ቀኙ ጋብቻ ከሚያዚያ 2011 ዓም እስከ 2014 ዓም ብቻ የቆየ መሆኑ በመሬቱ መጠቀም ላይ ተጠሪ የረዥም ጊዜ ተሳትፎ የሌላቸው መሆኑን በመጥቀስ የደረሰበት መደምደሚያ የግራ ቀኙን ማስረጃዎችና ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ህግ መሰረት ያደረገ ሆኖ ስላገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ውሳኔ

1. የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 46140 በቀን 10/09/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት አከራካሪውን 0.415 ሄክታር የእርሻ መሬት በተመለከተ የስር የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል የሰጠው ውሳኔና ይህንን ውሳኔ በማፅናት የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 408508 በቀን 24/09/2015 ዓ.ም እንዲሁም የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 424386 በቀን 08/10/2015 ዓ.ም የሰጡት ትዕዛዝ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስነስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9(1)(ለ) መሰረት ተሽሯል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

2. የነገሌ አርሲ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 44427 በቀን 08/06/2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስነስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9(1)(ሀ) መሰረት ፀንቷል፡፡
3. ግራ ቀኙ በሰበር ክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

**<u>ጉዳዩ ውሳኔ ስላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡</u>**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ/ጋ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መዝገብ ቁጥር 251970

ጥቅምት 06 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች፡- ወ/ት አባይነሽ ረጋሳ -ጠበቃ አቶ ተሸመ ንዳ ጋር -ቀርበዋል

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. ወ/ሮ ጥሩነሽ ረጋሳ
2ኛ. ወ/ሮ አበራሽ ረጋሳ } 2ኛ ተጠሪ የ1ኛ ተወካይ -ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ ኑዛዜን ለማሻር የቀረበ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክሱ በቀረበበት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ከሳሾች አመልካች ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ ተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ ይዘት፡- ግራ ቀኙ የሟች አቶ ረጋሳ ረጃቶ እና ወ/ሮ ሙላቷ ወ/ሚካኤል ወራሾች መሆናቸው በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አዲስ ከተማ ክፍል ከተማ ምድብ ችሎት በኮ/መ/ቁ 07974

መረጋገጡን ገልጸው ወላጆቻቻው በአዲስ አበባ ከተማ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 02 ውስጥ የሚገኝ የቤት ቁጥር1157 የሆነ የግል ቤት ትተው አልፈዋል፡፡ ይህ ቤት የሁሉም ወራሾች ድርሻ ሆኖእያለ አመልካች ለብቻቸው ይዘው እየተጠቀሙ ለማካፈል ፈቃደኛ ስላልሆኑ ውርስ እንዲጣራ ተጠሪዎች ላቀረቡት አቤቱታ አመልካች በሰጡት ምላሽ ሟች እናታቸው ወ/ሮ ሙላቷ ወ/ሚካኤል ለክርክሩ ምክንያት የሖነውን ቤት በጥቅምት 21 ቀን 2003 ዓ.ም በተደረገ ኑዛዜ ለአመልካች እዳስተላለፈችላት በመግለጽ ኑዛዜውንና የኑዛዜ ወራሽነቷን ያረጋገጠችበትን ማስረጃ አያይዞ አቅርባለች፡፡ ሟች እናታቸው ወ/ሮ ሙላቷ ወ/ሚካኤል አድርገዋል የተባለው ኑዛዜ በአባታቸው ድርሻ ላይ ጭምር መሆኑን ፤ ወራሾችን የነቀለ መሆኑን ፤ ኑዛዜው የሕጉን ፎርማሊቲ የማያሟላ በመሆኑና ሟች ኑዛዜውን ባደረጉበት ጊዜ እድሜያቸው ስለገፋ ኑዛዜውን በራሳቸው ህሊና ያደርጋሉ ተብሎ ስለማይገመት እንዲፈርስ እንዲወሰን ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ህዳር 14 ቀን 2015 ዓ.ም ለክሱ በሰጡት መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርበዋል፡፡ ሟች አባታቸው መጋቢት 21 ቀን 2000 ዓ.ም ስለሞቱ የአባታቸው የውርስ ጥያቄ በይርጋ ይታገዳል፡፡ በተመሳሳይ እናታቸው ወ/ሮ ሙላቷ ወ/ሚካኤል የሞቱት ግንቦት 30 ቀን 2009 ዓ.ም ሲሆን ተጠሪዎችን ወራሽነታቸውን አረጋግጠው ውርስ እንዲጣራላቸው አቤቱታ ያቀረቡት ከ5 ዓ.ም በኋላ ስለሆነ ከ3 ዓመት በኋላ የእናታቸውንም ውርስ ሊጠይቁ አይችሉም፡፡ ሟች ጥቅምት 21 ቀን 2003 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ የፎርማሊቲ ችግር የሌለው ከመሆኑም በተጨማሪ የሟች አርባ ነሐሴ 12 ቀን 2009 ወጥቶ በአከራካሪው መኖሪያ ቤት አመልካች እና ተጠሪዎች በተገኙበት ስለተነበበ ፤ አመልካቾች ኑዛዜው ሲነበብ በቦታው የነበሩ ቢሆንም በ15 ቀን ውስጥ ቅሬታቸውን ስላላቀረቡ የእናት ውርስ ድርሻን ሊጠይቁ አይችሉም፡፡  የቤቱ አካል የሆኑትን ሽንት ቤት እና ማዕድ ቤት ለማስመለስ ለክርክር እንዲሁም ለቤቱ እድሳት ያወጡትን ወጪ ተጠሪዎች ያልተጋሩት ቤቱ በኑዛዜ እንደተላለፈልኝ ስለሚያውቁ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያው ላይ ክርክር ሰምቶ የካቲት 29 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ብይን ተጠሪዎች በዋናነት ያቀረቡት አቤቱታ በኑዛዜው ተነቅለናል የሚል ሆኖ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 1123 ስር የተመለከተው የ10 ዓመት ይርጋ መሆኑን የሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 152134 አስገዳጅ ውሳኔ የሰጠ በመሆኑ ጉዳዩም ክፍፍል ያልተደረገ እና 10 ዓመት ያላለፈው መሆኑን ጠቅሶ የይርጋ መቃወሚያውን ውደቅ አድርጎ ፤ ግራ ቀኙ የሟች የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች ሲሆኑ ሟች ጥቅምት 21 ቀን 2003 ዓ.ም ባደረጉት ኑዛዜ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 02 የሚገኘውን የቤት ቁጥር 1157 ሙሉውን ለአመልካች፤ለ1ኛ ተጠሪ ደግሞ  ብር 200.00/ ሁለት መቶ/ እንዲሁም ለ2ኛ ተጠሪ ብር 500.00/ አምስት መቶ/ ተናዘዋል፡፡ ለተጠሪዎች ሟች አነስተኛ መጠን ያለው ገንዘብ ተናዘው ለአመልካች ቤቱን የተናዘዙት እየጦረችና እየተንከባከበች የምታኖረኝ ልጄ ናት በሚል ሲሆን ይጦረኛል/ይንከባከበኛል በሚል

ምክንያት ብቻ ሚች ካለው ንብረት አነስተኛ የሆነ ሀብት በመስጠት መንቀል የማይችል መሆኑን የፍትሐ ብሔር ሕጉ ድንጋጌ ማመላከቱን እና ኑዛዜው በሚች አቶ ረጋሳ ረጃቶ ድርሻ ላይ ጭምር የተደረገ መሆኑን ጠቅሶ ሚች ወ/ሮ ሙላቷ ወ/ሚካኤል ጥቅምት 21 ቀን 2003 ዓ.ም ደረጉት ኑዛዜ በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 913 እና 1123 ድንጋጌ መሠረት ፈራሽ ነው በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሰጠው ብይንና ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የይግባኝ አቤቱታውን በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሰረት ሰርዟል፡፡

የሰበር ቅሬታው የቀረበው የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት በሰበር ለማስለወጥ ሆኖ የአቤቱታው ይዘት በአጭሩ፡- የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረቡትን የይርጋ መቃወሚያ በብይን ውድቅ ያደረገው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት ኅዳር 24 ቀን 2011 ዓ.ም በሰበር መዝገብ ቁጥር 152134 የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሠረት በማድረግ እና የፍትሐ ብሔር ሕጉን ቁጥር 1123/3 ድንጋጌን በመጥቀስ ሲሆን ሰበር ሰሚ ችሎት በተጠቀሰው የመዝገብ ቁጥር ኑዛዜው ይፈርሳል በማለት የወሰነው በመዝገብ ላይ የተመለከቱት ተከራካሪዎች የሚች አባታቸው ኑዛዜ ሲነበብ በቦታው ያልነበሩ መሆናቸው በሥር ፍርድ ቤቶች በምስክሮች መረጋገጡን ጠቅሶ ሲሆን በተያዘው ጉዳይ ግን ኑዛዜው የተነበበው ተጠሪዎች፤ሌሎች ወራሾች፤አናዛዦች እና ቤተሰብ በተገኙበት ስለሆነ ተጠሪዎች በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 973/1 ድንጋጌ መሠረት ኑዛዜው አይጸናም በማለት በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ ሃሳባቸውን ስላልገለጹ፤እንዲሁም በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 973/3 ድንጋጌ መሠረት መግለጫውን ከሰጡበት ቀን አንስቶ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ክስ ለፍርድ ቤት አላቀረቡም በማለት ያቀረቡትን ክርክር የሚያስረዱ ምስክሮች ሳይሰሙ እና ተጠሪዎች ኑዛዜው ሲነበብ መኖር አለመኖራቸው ሳይጣራ በህጉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ያልቀረበን ክስ የሥር ፍርድ ቤቶች ተቀብለው ሚች ወ/ሮ ሙላቷ ወ/ሚካኤል ጥቅምት 21 ቀን 2003 ዓ.ም ደረጉት ኑዛዜ ይፈርሳል ማለታቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው፡፡ በተጨማሪም ተጠሪዎች ከውርስ ተነቅለናል በማለት ለፍርድ ቤት ያቀረቡት አቤቱታ አባታቸው ከሞቱ ከ14 ዓመታት በኋላ፤ እናታቸውም ከሞቱ 5 ዓመት ሞልቶ እያለ መልስ ሰጪዎች ሚች ወ/ሮ ሙላቷ ወ/ሚካኤል ያደረጉት የቁም ኑዛዜ የአባታችንን ድርሻ ስለምጨምር ይፍረስልን በማለት ያቀረቡትን ክስ ተቀብሎ የሥር ፍርድ ቤት ኑዛዜው እንዲፈርስ የሰጠው ብይን የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1000/1 ድንጋጌን ያላገናዘ ሆኖእያለ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህ ውሳኔ በመቃወም የቀረበውን የይግባኝ አቤቱታ መሰረዙ ተገቢ ባለመሆኑ ውሳኔ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 6/1 መሠረት ለሰበር ሰሚው ችሎቱ የተመራው አቤቱታ በሰበር ሰሚ ችሎቱ ተመርምሮ ተጠሪዎች ኑዛዜው ሲነበብ

የነበሩ መሆኑ አከራካሪ ባልሆነበት ኑዛዜው መጽናት የለበትም ከተባሉ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ የሆነው ከውርስ ነቅሎናል የሚለው የክርክር ዘንግ ብቻ ተወስዶ የይርጋ መቃወሚያው የመታለፉን አግባብነት የሰበር ሰሚ ችሎቱ በሰበር መዝገብ ቁጥር152134 እና በሰበር መዝገብ ቁጥር 82585 ከሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ አንፃር ጉዳዩን ለመመርመር የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪዎች ለሰበር አቤቱታው በሰጡት መልስ ተጠሪዎች ሟች እናታችን አደርጋዋለች የተባለው ኑዛዜ ስለመነበቡ የምናውቀው ነገር አለመኖሩንና ኑዛዜው ሲነበብ እንዳልሰማን ገልጸን ተከራክረን እያለ ኑዛዜው መነበቡን አምነን እንደተቀበልን በሰበር ሰሚ ችሎቱ ድምዳሜ ላይ መደረሱ ተገቢ አይደለም፡፡ ሟች ወ/ሮ ሙላቷ ወ/ሚካኤል ጥቅምት 21 ቀን 2003 ዓ.ም ኑዛዜ ማድረጓን ያወቅነው ተጠሪዎች ላቀረብነው የውርስ ይጣራልን አቤቱታ አመልካች ሰኔ 15 ቀን 2014 ዓ.ም በሰጠችው መልስ ነው፡፡ ኑዛዜው የተነበበው ተጠሪዎች ኑዛዜ እንዲፈርስ ክስ ካቀረብን ጥቅምት 07 ቀን 2015 ዓ.ም በኋላ ስለሆነ አመልካች ኑዛዜው ሲነበብ ተጠሪዎች እንደነበሩ እና ከተነበበ በኋላም በሕጉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ የኑዛዜ ይፍረስልን ክስ አልቀረበም የሚለው የአመልካች ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ በዋናነት ኑዛዜው እንዲፈርስ የጠየቅነው ስለነቀለንና በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1123 መሰረት ከሩብ በላይ ጉዳት አድርሶብናል በሚል ሲሆን ይህ ደግሞ ክፍፍልን ስለሚመለከት ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ድንጋጌ የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 973 ሳይሆን 1123/3/ ስር የተመለከተው የይርጋ ድንጋጌ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም፡፡ ተጠሪዎች ኑዛዜው በሟች አባታችን ድርሻ ጭምር የተደረገ ነው ከማለት ውጪ የሟች የአባታችንን ድርሻ ያልጠየቅን በመሆኑ በዚህ ረገድ በአመልካች የቀረበው የይርጋ መቃወሚያ ተቀባይነት የለውም፡፡ ተጠሪዎች ያቀረብነው ጥያቄ ኑዛዜ ይፍረስልን የሚል በመሆኑ አመልካች የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1000/1 እና (2) መሰረት በማድረግ ያቀረበችው የይርጋ ክርክር ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካችም የሰበር አቤቱታውቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለ መልኩ የተመለከተው የግራ ቀኝ ክርክር እና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ውሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንፃር የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለው ሕግ እና የሰበር ሰሚ ችሎቱ በጉዳዩ ላይ ከሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በፍትሐብሔር ሕጉ ቁጥር 1807/ረ/ ድንጋጌ መሠረት ይርጋ ግዴታዎችን ቀሪ ከሚያደርጉ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ነዉ። ድንጋጌው የውል ህግን የሚመለከት ቢሆንም **ግዴታዎች** ማለቱ የውል ግዴታን ብቻ ላለመሆኑ አመላካች ሲሆን ከቁጥር 1677/1 ድንጋጌ አንፃርም ሲታይ ሌሎች ግዴታዎችንም ይጨምራል። ይርጋ የመብት ጥያቄ በህጉ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ባለመቅረቡ በጊዜ ማለፍ ቀሪ የሚሆንበት፣ተጠያቅነትን በማስቀረት ያልነበረ መብትን የሚያጎናጽፍ ነው። ይርጋ ዳተኛ መብት

ጠያቅዎችን መብት የሚያሳጣ በአንፃሩ ባለዕዳው ሁልጊዜ ያለበትን ዕዳ እያሰበ በስጋት እንዳይኖር ነፃ የሚያወጣ ነው። በጊዜ ማለፍ ምክንያት ኃላፍነት ወርዶልኛል የሚለው ሰው ኃላፍንት እንዳለበት የማይክድ በክርክሩ በተከላሽነት የሚሰየመው ሰው ነው፡፡ ሕጉ ይህን መብት አንስቶ የመከራከር ዕድል ለባለዕዳው የተሰጠ ሆኖ መከራካሪውን ማንሳት የሚችለው በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መልክ ነው፡፡ የይርጋ መቃወሚያ ተጠቃሚ የሆነ ሰው በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 244/2 (ሠ) መሠረት በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ለማንሳት መብት ያለው ቢሆንም ይህን መብቱን መተው እንደምችል የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1856 ያስገነዝበናል። በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 244/2 (ሠ) እንዲሁም ከቁጥር 245 ድንጋጌዎች መረዳት እንደሚቻለውም ክሱ በይርጋ የታገደ መሆኑን የሚገልጽ መቃወሚያ ሲቀርብ የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ፍርድ ቤቱ ተቀብሎ ሌላው ተከራካሪ ወገን በጉዳዩ ላይ የሚያቀርበውን ክርክር ከሰማ በኋላ ውሳኔ ለመስጠት ተገቢ መስሎ የሚገምተው ማስረጃ እንዲቀርብለት በማድረግ መቃወሚያው በተገቢና በቂ ማስረጃ መደገፉን በመመርመር ተገቢ መስሎ የታየውን ብይን ሊሰጥ ይገባል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ክርክር የይርጋ መከራከሪ መብቱን ያልተጠቀመ ተከሳሽ መብቱን እንደተወው ስለምገመት ዳኞች ክርክሩን ማንሳት ስለማይችሉ ፍሬ ነገሩን መርምረው ውሳኔ ይሰጣሉ፡፡ የፍትሐብሔር ሕጉ ቁጥር 1851 ይርጋ የሚቋረጥባቸውን ምክንያቶች ይዘረዝራል፡፡ ይርጋ ከተቋረጠ እንደ አዲስ የሚቆጠር መሆኑን ከቁጥር 1852 ድንጋጌ መረዳት ይቻላል፡፡

ኑዛዜን በመቃወም የሚቀርበው ማናቸውም መቃወሚያ መታየት ያለበት አግባብነት ካለቸው የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች አንፃር ነው፡፡ የፍትሐ ብሔር ህግ ቁጥር 973 ስለ ኑዛዜ መነበብ እንዲሁም ኑዛዜው ሲነበብ የነበሩ ሰዎች ኑዛዜው እንዲፈርስ አቤቱታ የሚያቀርቡበትን ሥርዓት እና ጊዜውን በሚመለከት የሚደነግግ ሲሆን ይህ ድንጋጌ ኑዛዜው ከውርስ ነቅሎኛል /ነቅሎናል/ በማለት ኑዛዜው እንዲፈርስ የሚቀርብን ወይም የቀረበን አቤቱታን የሚመለከት አለመሆኑን የሰበር ሰሚው ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 152134 ላይ አስገዳጅ ውሳኔን ሰጥቷል፡፡
አንድ ኑዛዜ ፈራሽ ነው በሚል ስለሚቀርብ መግለጫ እና ክስ እንዲሁም መግለጫ እና ክሱ ሊቀርብ ስለሚገባበት የጊዜ ገደብ በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 973 እና 974 ተደንግጎ ይገኛል፡፡ የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 973 ድንጋጌ ኑዛዜው ፈራሽ ነው የሚል መቃወሚያ ያላቸው ኑዛዜው ሲነገር /ሲፌስ/ የነበሩትን ሰዎች የሚመለከት ነው፡፡ ይህም ኑዛዜው ሲነበብ የነበሩ ወይም የተወከሉ ሰዎች ኑዛዜው አይፀናም ወይም በኑዛዜው የተነገረ ቃል አይፀናም የሚሉትንና የመሳሰሉትን የሚቃወሙ ቢሆን ይህን ማድረግ ያለባቸው ኑዛዜው ከተነበበት አንስቶ እስከ አስራ አምስት ቀን ድረስ እንደሆነ ያመለክታል፡፡ የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 973/1 ድንጋጌ ክስን ሳይሆን መግለጫን የሚመለከት ነው፡፡ የንብረት ድልድል የማያውቅ ወራሽ መግለጫ የማቅረብ ግዴታ የለበትም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ክስን የማቅረብ ሃሣብ መግለጫው በጽሑፍ ካልሆነና ለአጣሪው ወይም ለዳኞች ወይም በውርስ ሊይ የተነሣውን ነገር

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ለመጨረስ ለተመረጡት የሽምግልና ዳኞች እንድደርስ ካልተደረገ በቀር እንደማይፀና /መቃወሚያ አለ ለማለት እንደማይቻል/ የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር
973/2/ ተደንግጓል፡፡ በመጨረሻም መግለጫው ከተሰጠበት ቀን አንስቶ እስከ ሦስት ወር ድረስ ክስ ካልቀረበ መብቱ ከነጭራሹ እንደሚቀር በንኡስ ቁጥር /3/ ተመልክቷል፡፡ ኑዛዜ መኖሩን ማወቅ እና በኑዛዜው የተደረገውን ክፍፍል ይዘት ማወቅ ልዩነት ያለው መሆኑን ልብ ማለት ይገባል፡፡ ኑዛዜው ሲነበብ(ሲፈስ) በአካል ወይም በተወካይ ላልተሳተፉ ወይንም በሌሉበት ኑዛዜ የፈሰሰ ሰዎች በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 973 የተመለከተው ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው የውርስ አጣሪው ስለ ክፍያ ፤ ድልድል አመዳደብ ሃሳብ ከነገራቸው ቀን አንስቶ መሆኑን የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 974/1 ድንጋጌ ያመለክታል፡፡ አንድ ሰው ኑዛዜው መነበቡን (መፍሰሱን) ያውቃል ለማለት በአካል ወይንም በተወካይ ኑዛዜው ሲነበብ ወይም ሲፈስ መገኘት አልያም ስለ ክፍያ፤ድልድል አመዳደብ ሃሳብ በአጣሪው የተነገረው እንደሆነ መሆኑን ከፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 973 እና 974/1 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ኑዛዜ ከፈሰሰበት ወይም ሟቹ ከሞተበት ከአምስት ዓመት በኋላ ስለኑዛዜው መጽናት፤ስለክፍያው አመዳደብ አጣሪው ያቀረበውን ሃሳብ መቃወሚያ ሊቀርብበት እንደማይገባ በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 974/2 ሥር ተመልክቷል፡፡ ኑዛዜ ስነበብ(ሲፈስ) በአካል ያልነበሩ፤ያልተወከሉ አልያም ስለ ክፍያ፤ድልድል አመዳደብ ሃሳብ በአጣሪው ያልተነገራቸው ሰዎችን የሚመለከተው ይርጋ በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 974/2 ሥር የተመለከተው የይርጋ ድንጋጌ መሆኑን ይህን ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 217691(ያልታተመ) ሰኔ 30 ቀን 2014 ዓ.ም አስገዳጅ ውሳኔን ሰጥቷል፡፡ ኑዛዜ ከፈሰሰ(ከተነበበ) ከ5 ዓመት በኋላ ስለኑዛዜ መጽናት ሆነ ስለክፍያ ድልድል መቃወሚያ ማቅረብ እንደማይቻል  የሰበር ሰሚ ችሎቱ በሰበር በመዝገብ ቁጥር 36604(በቅጽ 8 እንደታተመው) አስገዳጅ ውሳኔን ሰጥቷል፡፡

ከውርስ መንቀል ተናዛዡ ምክንያቱን በመግለፅ ወይንም በዝምታ ከወራሾቹ ውስጥ አንዱን ወይንም ከአንድ በላይ የሆኑትን በውርሱ እንዳይካፈሉ የውርስ ህጉን መሰረት አድርጎ ኑዛዜ ማድረግን የሚመለከት ነው፡፡ ከፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 937 — 940 ካሉት ድንጋጌዎች መረዳት እንደሚቻለው የመንቀል ዓይነቶቹ በግልጽ ፣ በዝምታ እና በተዘዋዋሪ መንገድ ሊሆን ይችላል፡፡ በተዛዋዋሪ መንገድ መንቀል ኑዛዜ አላደረገም እንዳይባል ብቻ እዚህግባ የማይባል ከውርስ የመንቀል ውጤት ያለው ድርሻን ከውርስ ሃብቱ ለወራሹ መስጠት መሆኑን የሰበር ሰሚ ችሎቱ በሰበር መዝገብ ቁጥር 57836 ፤ 58338 እና በሌሎች መዛግብት ላይ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

በኑዛዜ የሚከናወኑት ተግባሮች የኑዛዜ ስጦታ (legacy) ወይንም የክፍያ ደንብ (Rule of partition) ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በመርህ ደረጃ አንድ ሰው ከውርስ ሀብቱ መካከል አንድን ንብረት ለወራሾቹ መስጠቱ የኑዛዜ ስጦታ የማያሰኘው ሲሆን፤ይልቁንም ይህ ዓይነቱን ኑዛዜ ሕጉ የሚቀበለው እንደ አንድ የክፍያ ደንብ በመሆኑ አንድ አውራሻ ለወራሹ አንድን ንብረት ቢናዝዝለት የኑዛዜ ስጦታ(legacy) አፈፃፀምን

መከተል ሳይሆን የክፍያ ደንብ (Rule of partition) በመከተል የሚከናወን ይሆናል፡፡ ነገርግን በኑዛዜው ላይ የሚሰጠው የክፍያ መጠን በመግለፁ ብቻ ሁል ጊዜ የክፍያ ደንብ የሚባል ባለመሆኑ በኑዛዜው ላይ የሰፈረው የንብረት መጠን ከሟቹ የውርስ ሀብት ግምት ጋር ታይቶ የመነቀል ወይስ የክፍያ ማነስ የሚለው ውጤቱ የሚለይ ይሆናል፡፡

ኑዛዜ ስጦታን (legacy) የሚመለከት ከሆነ በፍትሐ ብሔር ህጉ አንቀጽ 942 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሠረት ውርስ በማጣራት (liquidation) በሕጉ ከቁጥር 1037 — 1051 መሠረት በተለይም በቁጥር 1047/3 ድንጋጌ መሠረት በስጦታ እንዲተላለፍ የተባለው ንብረት ግምት ለተጠቃሚው በቅዲሚያ የሚሰጥ ሲሆን ፤ የክፍያ ደንብ (Rule of partition) ደግሞ የፍትሐ ብሔር ሕጉን ቁጥር 1060 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሠረት የሚከናወን ነው፡፡ አባት ፤ እናት ወይንም ሌሎች ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆች ለልጆቻቸውና ሌሎች ወደ ታች ለሚቆጠሩ ተወላጆች ሀብታቸውን ለመስጠት እና ለማከፋፈል የሚችሉ ሲሆን ይህ የክፍፍል ሥርዓት አንድን ተወላጅ ከሚደርሰው ከሩብ የበለጠ ጉዳት አድርሶበት ከሆነና በስጦታ አከፋፈሉ ውስጥ ተቃራኒ ቃል ከሌለ በቀር የስጦታ አከፋፈሉ እንዲቀር መጠየቅ የሚችል መሆኑን የፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 1123/1 ድንጋጌ ያመለክታል፡፡ ይሕን የስጦታ ክፍያ ቀሪ እንዲሆን የሚቀርብ ክስ ስጦታ አድራጊ ወላጅ በሞተ በሁለት ዓመት ፤ የስጦታ ክፍፍሉ ከተደረገበት አንስቶ በ10 ዓመት ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ቀሪ እንደሚሆን የፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 1123/3 ይደነግጋጋል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪዎች የዳኝነት ጥያቄ ሟች እናታቸው ወ/ሮ ሙላቷ ወ/ሚካኤል ጥቅምት 21 ቀን 2003 ዓ.ም አደረጉ የተባለው ኑዛዜ ፎርማሊትን ያልጠበቀ፤ተጠሪዎችን ከውርስ የነቀለ ከሕግ ውጪ የተደረገ ነው ተብሎ ፈራሽ እንዲሆን የጠየቁ ሲሆን ኑዛዜ የፊርማሊት ችግር የሌለው ከመሆኑም በተጨማሪ የሟች አርባ ነሐሴ 12 ቀን 2009 ዓ.ም ወጥቶ በአከራካሪው መኖሪያ ቤት አመልካች እና ተጠሪዎች በተገኙበት ስለተነበበ ተጠሪዎች ኑዛዜው ሲነበብ በቦታው ስለነበሩ በሕጉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ መቃወሚያ አላቀረቡም በማለት አመልካች ላነሱት ክርክር ተጠሪዎች በሰጡት ምላሽ የተነበበው ኑዛዜ ሳይሆን የምርቃት ወረቀት ነው በማለት የተከራካሩ መሆኑን በችሎቱ ትዕዛዝ የመጣው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መዝገብ ያመለክታል፡፡ የተጠሪዎች ጥያቄ የኑዛዜ ፈራሽነትን የሚመለከት እንጅ የስጦታ ክፍያ ደንብ እንድፈርስ ስላልሆነ የፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 1123/3 ድንጋጌ ለጉዳዩ ተገቢነት የለውም፡፡ ኑዛዜው ሲነበብ(ሲፈስ) የነበሩ ወይም ኑዛዜው ስነበብ(ሲፈስ) በአካል ያልነበሩ፤ያልተወከሉ አልያም ስለ ክፍያ፤ድልድል አመዳደብ ሃሳብ በአጣሪው ያልተነገራቸው ሰዎች ኑዛዜው እንዲፈርስ አቤቱታ የሚያቀርቡበትን ሥርዓት እና የይርጋ ጊዜውን በሚመለከት ተገቢነት ያለው ድንጋጌ የፍትሐ ብሔር ህግ ቁጥር 973 እና 974/2 መሆኑን የሰበር ሰሚው ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር152134 ላይ የሰጠውን አስገዳጅ ውሳኔ በሚቃረን መልኩ ተጠሪዎች ጥቅምት 21

ቀን 2003 ዓ.ም ሟች እናታቸው ወ/ሮ ሙላቷ ወ/ሚካኤል ያደጉት ኑዛዜ ፈራሽ እንዲሆንላቸው ያቀረቡትን ዳኝነት ወደ ጎን በመተው ኑዛዜው ከውርስ ይነቅለናል በማለት ያቀረቡት አንድ የክርክር ዘንግ ላይ አላግባብ ነጥሎ በመውሰድ ተጠሪዎች ኑዛዜው ስነበብ(ሲፈስ) በአካል የነበሩ መሆን/አለመሆኑ ወይም መወከል/አለመወከላቸው ሳይጣራ ያቀረቡት ክስ በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 1123/3 መሠረት በይርጋ አይታገድም ማለቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ ቀጣዩ ተወስኗል፡፡

**ውሳኔ**

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 102446 የካቲት 29 ቀን 20115 ዓ.ም የሰጠው ብይን ፤ እንዲሁም ሚያዝያ 24 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ እና ትዕዛዝ ፤ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 307965 ሰኔ 30 ቀን 2016 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ብይን በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ- ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 9/1(ለ) መሠረት **ተሸሯል**።
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በውሳኔ የዘጋውን የመዝገብ ቁጥር 102446 አንቀሳቅሶ ሟች ወ/ሮ ሙላቷ ወ/ሚካኤል ጥቅምት 21 ቀን 2003 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ አመልካቾች በተገኙበት መነበብ/አለመነበቡን፤ኑዛዜው ስነበብ(ሲፈስ) መወከል አለመወከላቸውን ፤የመነበብ ወይንም አለመነበቡን ውጤት ከፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 973 እና 974 ድንጋጌዎች እና ሌሎች ለጉዳዩ ተገቢነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት አድርጎ በማጣራት ይሕ መቃወሚያ የሚታለፍበት የሕግ መሠረት ካለ ቀሪ ክርክሮችን ተመልክቶ ተገቢ ውሳኔ እንዲሰጥ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 9/2 መሠረት መዝገቡ ተመልሶለታል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. የሥር ፍርድ ቤት መዝገብ በመጣበት አግባብ ወደ መጣበት ፍርድ ቤት ይመለስ ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መ/ቁ 252154
ጥቅምት 04 ቀን 2017 ዓ/ም

**ዳኞች:-**ሽመክት አሰፋ

ገበየሁ ፈለቀ

ዓለማየሁ ሹናራ

ተናኘ ጥላሁን

ዘዉዲቱ ታደሰ

የሰበር አመልካቾች 1.ወ/ሮ አስናቀናች ኃ/ማርያም

2. ሰሎሞን መኮንን ደበላ
3. ኃ/ጊዮርጊስ መኮንን ደበላ
4. አለማየሁ መኮንን ደበላ
5. ኤልሳቤጥ መኮንን ደበላ

አልቀረቡም

የሰበር ተጠሪዎች 1ኛ. የኮ/ቀ/ክ/ከ የመሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት

2ኛ. የኮ/ቀ/ክ/ከ ወረዳ 2 የመሬት ልማት አስተዳደር ጽ/ቤት

አልቀረቡም

መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ፍርድ

ጉዳዩ የሁከት ይወገድልኝ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን በስር ፍርድ ቤት አመልካቾች ከሳሽ የነበሩ ሲሆን ተጠሪዎች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

አመልካቾች በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያቀረቡት የክስ ይዘት በአጭሩ፡- በኮ/ቀ/ክ/ከ ወረዳ 02 ክልል ውስጥ በቤት ቁጥር 1105 በሆነው ቤት ግማሹ የ1ኛ አመልካች ሲሆን ቀሪው ከ2ኛ እስከ 5ኛ አመልካቾች (ወራሾች) ጋር በመሆን ከሟች አቶ መኮንን ደበላ በዉርስ ያገኘነውን ቤት እና ይዞታ ተጠሪዎች ለመንገድ ግንባታ ይፈለጋል በሚል በአዋጅ ቁጥር 1161/2011 አንቀጽ 26/1 መሠረት እና በደንብ ቁጥር 472/2012 እና በመመርያ ቁጥር 79/2014 አንቀጽ 9/ሀ/ለ መሰረት ተገቢውን የንብረት ካሳ ሳይከፍሉ ቤት እናፈርሳለን በማለት ከፍተኛ ሁከት እየፈጠሩ በመሆኑ ንብረታችን በልማት የሚፈለግ ከሆነ ተገቢው ካሳ እስከሚከፈለን ጊዜ ድረስ ከዚህ የሁከት ድርጊታቸው እንዲታቀቡልን እና የፈጠሩብን የሁከት ድርጊት እንዲወገድልን የሚል ነው፡፡

ተጠሪዎች በሰጡት መልስ በአዋጅ ቁጥር 1183/2012 መሰረት አመልካቾች ለአስተዳደሩ ያላቸውን ቅሬታ ሳያቀርቡ በቀጥታ ያቀረቡትን ክስ እንዲሁም ጉዳዩ ከካሳ ክፍያ ጋር የተያያዘ ስለሆነ አመልካቾች ይህን ክስ በአስተዳደሩ ለተቋቋመው ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ከሚያርቡ በስተቀር ፍ/ቤቱ ተቀብሎ ለማከራከር የሚያስችል ስልጣን የለውም የሚሉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አንስተው በፍሬ ነገር ላይ ደግሞ በመንገድ ልማት ምክንያት በይዞታቸው ላይ ለነበረው ንብረት በህጉ በተቀመጠው አግባብ በወቅቱ በነበረው መመርያ ቁጥር 19/2006 መሰረት ተገቢው ካሳ ተከፍሏቸዋል፡፡ በዚህም መሰረት ካላቸው ይዞታ ላይ በከፊል ለተወሰደባቸውና በይዞታው ላይ ለነበረው የፈረንጅ ፅድ ፤አቮካዶ እና ጫት ወቅቱ መመሪያ በሚፈቅደው መሰረት ብር 1,128,128 /አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሀያ ስምንት ሺህ አንድ መቶ ሀያ ስምንት ብር / ተከፍሏቸዋል፡፡ ለንብረቱ የተተመነላቸውን ካሳ ተስማምተውና ፈቅደው የወሰዱ ሲሆን በወቅቱ ያቀረቡት ቅሬታ የለም ፤ ከሁለት አመት ቆይታ በኃላ በመንገዱ ልማት ምክንያት ካሳ ሳይከፈለን ቤት አፍርሱ ተብሎ የቃል ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶናል ሲሉ ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለውም፡፡ ስለግንባታው ህጋዊነት ስልጣን ካለው አካል የተሰጠ ማስረጃ ካልቀረበ ለንብረቱ ካሳ ሊከፈል ስለማይችል የይዞታ ማረጋገጫ ሰነዱ እና የአየር ካርታም ይህንኑ የሚያጠናክር በመሆኑ ቀድሞውኑ ማስጠንቀቂያ ሰጥተን ተገቢውን ካሳ ከፍለን ያስለቀቅነው እና ካሳ ተቀብለው በለቀቁት ቦታ ላይ ክስ የማቅረብ መብትም አይኖራቸውም የሚል መልስ አቅርቧል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ጉዳዩ በዚህ መልክ የቀረበለት የስር ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ለአመልካቾች ወላጅ አባት ከአሁን በፊት በዚህ ይዞታ ላይ ካሳ የተከፈለ ስለመሆኑ በጊዜው ካሳ በሚከፈለበት ወቅት በቦታው ላይ ህጋዊ የሆነ እና በአየር ካርታ የሚታይ ግንባታ ባለመኖሩ የቤት ካሳ ክፍያ እንዳልተሰጠ ማስረጃ መቅረቡን፤ አመልካቾችም በዚህ ቦታ ላይ ህጋዊ ቤት እንደነበራቸው እና ተገቢው ካሳ ያልተከፈላቸው ቢሆን ኖሮ በወቅቱ ጥያቄ የማያነሱበት አሳማኝ ምክንያት ባለመኖሩ የቀረቡት ማስረጃዎች በሰዓቱ የተከፈለው ካሳ ክፍያ ይዞታውን የሚያጠቃልል ስለመሆኑ የሚያስረዱ በመሆናቸው በፍ/ህ/ቁ 1140 ድንጋጌ መሰረት አመልካቾች ቀድሞ ካሳ በተከፈለበት ይዞታ ላይ በእውነት ለማዘዝ እና የህግ ጥበቃ ሊሰጠው የሚችል ህጋዊ የይዞታ መብት የሌላቸው በመሆኑ ተጠሪዎች የፈጠሩት የሁከት ድርጊት የለም በማለት ክሱን ውደቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር የተሰኙት የሰበር አመልካቾች ቅሬታቸውን በይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ አግባብነት ያለው ነው በማለት ቅሬታቸዉን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 337 መሰረት ሰርዟል፡፡

የሰበር ቅሬታው የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ሲሆን አጭር ይዘቱም፡- የሰበር አመልካቾች ሁከት የተነሳበትን ቤት ከነ መኪና ማጠቢያ ላቢያጆ የግንባታ ፈቃድ ተሰቶን የሰራነው በ1998 ነው፡፡ የልማት ተነሺዎችን ካሳ አከፋፈል በተመለከተ በ2011 በወጣው አዋጅ ቁ.1161/2011 ደንብ ቁ.472/2012 እና በመመሪያ ቁ.79/2014 አንቀጽ 9/1/ሀ/ኘ/ አንቀጽ 8/1/ሐ መሠረት የግል ይዞታ ለልማት ተፈልጎ ተነሺ ሲሆን በይዞታው ላይ ለሚገኝ ንብረት በሙሉ ካሳ መከፈል እንዳለበት እንደሚደነግግ ቤቱ በ1997 የአየር ካርታ ላይ ይታያል አይታይም? የሚለው ክርክር ሊነሳ ይችል የነበረው በድሮው አዋጅ ቁ.455/1997 በመመርያ ቁ.19/2006 መሠረት ብቻ ነው እንጂ በአዲሱ አዋጅ እንዳልሆነ፤ ለቤቱ በአዲሱ አዋጅ 1161/2011 መሰረት መመሪያ ቁ 79/2014 ሲወጣ እንደሚከፍሉን በወቅቱ ቃለ ጉባኤ ይዘን ተስማምተናል፡፡ የሰበር ተጠሪዎች በቤቱ ላይ የህገወጥነት ክርክር ባላቀረቡበት እና ቤቱም በግልጽ በይዞታው ላይ እንደሚገኝ በቀን 18/09/2015 የፅሁፍ መልስ በሰጡበት ሁኔታ የተሻረ አዋጅን መሰረት አድርጎ 1997 አየር ካርታ ላይ ስለማይታይ በማለት የሰጠው ዉሳኔ ተገቢነት የሌለው ነው፡፡ የሰበር አመልካቾች የግንባታ ፈቃዱን አግኝተናል በማለት ለትክክለኛ ፍትህ ይረዳ ዘንድ በአቤቱታ ለማያያዝ ብንጠይቅም የስር ፍ/ቤትም አቤቱታችንን ባለመቀበል የማስረጃ ህጉን በተጻረረ መልኩ የሰጠው ዉሳኔ እና የከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህንኑ አለማረሙ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡ መልስ ሰጪዎችም ህገ ወጥ ግንባታ ነው ባላሉበት እራሳቸው አያይዘው ባቀረቡት ካርታ ላይ በግልጽ አካተዉት እያለ በህጋዊ

ይዞታው ውስጥ ለሚገኝ ማንኛውም ቋሚ ማሻሻያ ተገቢውን ካሳ መክፈል ሲገባቸው ሁከት ለመፍጠር መንቀሳቀሳቸው ተገቢ አይደለም በሚል ሁከቱ እንዲወገድ ማዘዝ ሲገባው ጉዳዩን በጥልቀት ሳይመረምር ህጋዊ ጥበቃ የለውም በሚል የሰጠው ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲታረምልን የሚል ይዘት ያለው ነዉ፡፡

የሰበር ችሎቱም ጉዳዩን መርምሮ አመልካቾች ያቀረቡት ክስ ቤት ለማፍረስ ያደረገው እንቅስቃሴ የሁከት ተግባር ነው በሚል የቀረበ ክስ ላይ ካሳ ተከፍሎበታል ተብሎ በተጠሪ በኩል የቀረበው ክርክርና ማስረጃ በመቀበል የተሰጠው ውሳኔ እንዲፈርስ የተባለው ቤት ጨምሮ ካሳ የተከፈለ መሆን አለመሆኑ እና ቀድሞ በቦታው ላይ ቤት መኖር አለመኖሩ ተረጋግጦ ነው ወይስ አይደለም የሚለው እና ተያያዥ የክርክር ጭብጥ ተይዞ ግራ ቀኙ ክርክር እንዲያደርጉበት ታዞ የጽሁፍ ክርክር አድርገውበታል፡፡

1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በቀን 27/09/2016 ዓ/ም የተጻፈ 04 ገጽ መልሳቸውን ያቀረቡ ሲሆን አጭር ይዘቱም፡- አዋጅ ቁጥር 1161/2011 በ2011 ዓ.ም ቢወጣም አመልካቾች የካሳ ክፍያ በተከፈላቸው ጊዜ  አስተዳደሩ ይጠቀምበት የነበረው በመመሪያ ቁጥር 19/2006 ነው፡፡ በዚህም መመሪያ መሰረት ለልማት የተፈለገው ይዞታ ካሳ ተከፍሎበታል እነዚህ ይዞታዎችም በአመልካች እጅ ውስጥ ይሁኑ እንጂ 2013 ለይዞታው ካሳ ሲከፈል እነዚህ ቤቶች የግንባታ ፈቃድ ስለሌላቸውና በ1997 የአየር ካርታ ላይ ስለማይታዩ በይዞታ ማረጋገጫ ሰነዱ ላይም ያልተካተቱ በመሆናቸው ካሳ አልተከፈለባቸውም፡፡ በልማት በተፈለገው ይዞታ ላይ ባለው ሌሎች ንብረት ላይ ግን ካሳ መከፈሉን፤ በመሆኑም ይዞታው ለልማት ሲፈለግ ግንባታን ለማፍረስ ስንቀሳቀስ ካሳ ሳይከፈለን ቤቶችን ማፍረስ ሁከት ነው  በማለት ያቀረቡት አቤቱታ በስር ፍ/ቤት በአግባቡ ውሳኔ ስለተሰጠበት ውሳኔው እንዲጸናልን፤ የሰበር አመልካቾች በአዋጅ ቁጥር 1161/2011 መሰረት መስተናገድ አለብን በማለት ቅሬታቸውን ማቅረብ የነበረባቸው በዚሁ አዋጅ ቁጥር አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ አንድ መሠረት በ30 ቀናት ውስጥ ስለሆነ  በይርጋ የሚታገድ ነው፡፡ ለዚህ ፍ/ቤት ባቀረቡት ቅሬታ በስር ፍ/ቤት ያልተከራከርንበትና ማስረጃም ሆነ አስተያየት ያልሰጠንበት ሲሆን ማስረጃ እንዳናቀርብ ተከልክለናል በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ አመልካቾች በአሁኑ ሰአት ይዞታው በእጃቸው ይሁን እንጂ በ2013ዓ.ም ለልማት የተፈለገው ይዞታ ላይ ካሳ የተከፈለ በመሆኑ ካሳ በተከፈለበት ይዞታ ላይ የሁከት ክርክር ማንሳት የማይቻል በመሆኑ አቤቱታቸውን ውድቅ በማድረግ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲያጸናልን  የሚል ይዘት ያለው ክርክር አቅርበዋል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የሰበር አመልካችም የሰበር ቅሬታቸዉን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርበዉ ክርክሩ በዚሁ ተጠቃሏል፡፡

በአጠቃላይ የግራቀኙ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭር በአጭሩ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎትም ቅሬታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ ግራ ቀኙ በስር ፍርድ ቤት ካደረጉት ክርክር የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እና አግባብነት ካለዉ ህግ ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን መርምሯል ፡፡ እንደመረመረውም ቅሬታዉ ያስቀርባል ሲባል የተያዘዉ ጭብጥ ተጠሪዎች ቤት ለማፍረስ ያደረጉት እንቅስቃሴ የሁከት ተግባር ነዉ በሚል የቀረበ ክስ ላይ ካሳ ተከፍሎበታል ተብሎ በተጠሪ በኩል የቀረበዉ ክርክር እና ማስረጃ በመቀበል የተሰጠዉ ዉሳኔ እንዲፈርስ የተባለዉ ቤት ጨምሮ ካሳ የተከፈለ መሆን አለመሆኑ እና ቀድሞ በቦታዉ ላይ ቤት መኖር አለመኖሩ ተረጋግጦ ነወይ የሚለዉ እና ተያያዥ የክርክር ጭብጥ ተይዞ በማጣራት ረገድ የተፈጸመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን ለመመርመር በመሆኑ ከዚሁ ጭብጥ አንጻር ጉዳዩን እንደሚከተለዉ መርምረናል ፡፡ እንደመረመርነዉም የሰበር አመልካቾች ካሳ ያልተከፈለበትን ቤት ተጠሪዎች ለማፍረስ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ሁከት እየፈጠሩብን ስለሆነ ሁከት ይወገድልን በማለት የሚከራከሩ ሲሆን የሰበር ተጠሪዎች ደግሞ አስቀድሞ ለጠቅላላ ይዞታዉ ካሳ የተከፈለበት ስለሆነ አመልካቾች የሁከት ክርክር ማንሳት አይችሉም፡፡ ፧ለህገ ወጥ ግንባታም ካሳ ሊከፈል የሚችልበት ምክንያት የለም በማለት የሚከራከሩ ናቸዉ ፡፡ በመሰረቱ በተጠሪዎች በኩል እንዲፈርስ ለተባለዉ የአመልካቾች ቤት ካሳ ተከፍሎበታል የሚል ክርክር የላቸዉም ፡፡የሚከራከሩት በህጋዊ መንገድ ካርታ እና ፕላን እንዲሁም የግንባታ ፈቃድ ሳይኖረዉ የተገነባ ህገ ወጥ ግንባታ ስለሆነ በወቅቱ በ2013 ዓም በነበረዉ መመሪያ ቁጥር 19/2006 መሰረት ካሳ ሊከፈልበት የሚችል አልነበረም በወቅቱ ህጋዊ ለሆነዉ ይዞታቸዉ ግን ሊከፈላቸዉ የሚገባዉ ካሳ ተከፍሏቸዋል በማለት ነዉ ፡፡ የሰበር አመልካቾች ግንባታዉ ህጋዊ እንደሆነ አደርጎ ከመከራከር ዉጭ ይህንኑ ለማረጋገጥ ያቀረቡት ማስረጃ አለመኖሩን ተመልክተናል ፡፡ አመልካቾች ለቤቱ በአዲሱ አዋጅ 1161/2011 መሰረት መመሪያ ቁ 79/2014 ሲወጣ እንደሚከፍሉን በወቅቱ ቃለ ጉባኤ ይዘን ተስማምተናል ይበሉ እንጅ ይህንን የሚያሳይ ቃለ ጉባኤ መኖሩን በስር ፍርድ ቤት እንዲቀርብ አድርገዉ አላረጋገጡም እንጅ ቢረጋገጥ እንኳን በወቅቱ በነበረዉ ህግ እና መመሪያ በሚፈቅደዉ አግባብ ለህጋዊ ንብረታቸዉ ካሰ ከወሰዱ በኋላ በወቅቱ ህገ ወጥ ነዉ ተብሎ ካሳ ያልተከፈለበትን ቤት እንደገና አዲስ ህግ ስለወጣ ካሳ ሊከፈለን ይገባል በማለት የሚቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የሚኖረዉ አይደለም ፡፡ በመሰረቱ አንድ ግዴታ እንዲፈጸምለት የሚጠይቅ ሰዉ ለግዴታዉ መኖር

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ህ/ቁ 2001 እንዲሁም በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 258 እስከ 261 ከተለከቱት ድንጋጌዎች መረዳት የሚቻል ነዉ፡፡ በፍታብሄር ጉዳይ እያንዳነዱ ተከራካሪ ወገን በክርክሩ ረቺ ሊሆን የሚችለዉ ተገቢዉን ማስረጀ አቅርቦ በእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት ክርክሩን ከሌላኛዉ ተከራካሪ ወገን በተሻለ ሁኔታ አስረድቶ በተገኘ ግዜ ነዉ፡፡ በያዝነዉ ጉዳይ ማስረጃን የመመዘን እና ፍሬ ነገርን የማጣራት ስልጣን በተሰጣቸዉ  የስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠዉ ፍሬ ነገር ለሰበር አመልካቾች ለህጋዊ ይዞታዉ ብር 1,128,128 /አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሀያ ስምንት ሺህ አንድ መቶ ሀያ ስምንት ብር /  በ20013 ዓም ካሰ የተከፈላቸዉ መሆኑ እና ቀሪ ለህጋዊ ንብረት ያልተከፈለ ካሳ አለመኖሩ ነዉ፡፡ ስለዚህ ካሳ በተከፈለበት ህጋዊ ይዞታ ዉስጥ ቤት ነበረበት በሚል ምክንያት የቤቱን ህጋዊነት በወቅቱ አረጋግጠዉ ካሳዉን መዉሰድ ሲገባቸዉ አልፈዉ እንደገና  አሁን አዲስ ህግ ወጥቷል የሚል መነሻ  ይዘዉ በወቅቱ ካሳ የከፈለዉ አካል ይዞታዉን ለተፈለገበት ዓላማ ለማዋል አፈርሳለሁ ብሎ ሲንቀሳቀስ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1140 እና 1149 ደንጋጌዎችን በመጥቀስ ሁከት ይወገድልኝ ክርክር ማቅረብ የሚችሉበት ህጋዊ ሁኔታ የለም፡፡ ምክንያቱም ይዞታዉንም ሆነ አከራካሪዉን ቤት በእጅ አድርገዉ በዕዉነት የሚያዙበት ደረጃ ላይ ባለመሆናቸዉ ነዉ፡፡

የዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣንም መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉን ዉሳኔዎች በማረም ላይ የተገደበ ስለመሆኑ የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80 (3-ሀ) እንዲሁም የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 4 እና 10 ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻል ነዉ፡፡በመሆኑም  የስር ፍርድ ቤቶች ማስረጃን መዝነዉ የደረሱበትን የፍሬ ነገር ድምዳሜ ሰበር ሰሚ ችሎት  በድጋሚ ሊመረምር የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡

በአዋጅ ቁ.1234/2013 በትርጉም ክፍል አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለዉ አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን፣ ህግ ያላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉን ህግ የሚጠቅስ፣ ለክርክሩ አግባብነት ያለዉ ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለዉ ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፣ በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ዉድቅ በማድረግ የተወሰነ፣ በፍርድ አፈፃፀም ሂደት ከዋናዉ ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትዕዛዝ የተሰጠበት፣ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተወሰነ፣ የአስተዳደር አካል ወይም ተቋም ከህግ ዉጭ የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ በመቃረን የተወሰነ ሲሆን ነዉ፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በተያዘዉ ጉዳይ የስር ፍርድ ቤቶች በሰጡት ዉሳኔ ላይ ከላይ የተጠቀሱትን በህጉ የተመከቱትን መስፈርቶች የጣሱ ስለመሆኑ የዉሳኔዉ ይዘት የሚያሳይ ባለመሆኑ ስር ፍረድ ቤቶች የተሰጠዉ ዉሳኔ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም ፡፡

በመሆኑም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 308931 ሰኔ 02 ቀን 2015 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 308216 ሐምሌ 03 ቀን 2015 ዓ/ም በትእዛዝ የጸናዉ ፍርድ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም ተብሎ በፍብ/ስ/ስህ/ቁ 348(1) ጸንቷል ፡፡

የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
## የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ.መ.ቁጥር 252163

ቀን ጥቅምት 06ቀን 2017ዓ/ም

**ዳኞች፡-** ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ብርሃኑ መንግስቱ

ማርታ ተካ

**አመልካች**:- አቶ መንግስቱ ደምሴ

**ተጠሪዎች**፡-1. ካራ ቆሬ ሪልእስቴት ኃ/የተ/የግ/ማህበር

2. የቦሌ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት

3. ወ/ሮ ብርቋ ተካ

4. አቶ አህመድ መሀመድ

5. አቶ አብዱልመሰድ ነጋሽ

6. አቶ መንሱር ሱልጣን

7. አቶ ሀብታሙ ከፍያለው

8. አቶ እስማኤል ጉዮ

9. አቶ ኢሳያስ ሀይሌ

አልቀረቡም

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

10. ኤድካሄ ሪል እስቴት ዴቨሎፐር ኃ/የተ/የግ/ማህበር

11. አስ ኤች ኤን ኤኢኤች ኤ ትሬድንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው የከተማ ይዞታን የተመለከተ ጉዳይ ሲሆን የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍ/ቤት አመልካች ከሳሽ፤ 1ኛ ተጠሪ ተከሳሽ ሲሆን ሌሎች ተጠሪዎች ጣልቃ ገቦች ነበሩ፡፡ የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 128554 መጋቢት 20 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በተሰጠ ትዕዛዝ የጸናዉ ብይን መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በሚል ነዉ፡፡

በስር ፍ/ቤት አመልካች ያቀረቡት የክስ ይዘት፡- የአመልካች ወላጆች በነባር አርሶ-አደርነት ግብር በስማቸው እየከፈሉ ሲጠቀሙበት ከቆዩ በኋላ ወደ አመልካች በውርስ ተላልፎልኝ በእጄ የሚገኘው በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 12 ልዩ ቦታው መጀሌ/ማሪያም ማዞሪያ ሰፈር የሚባል አካባቢ የሚገኝ 50,000 ካሬ ሜትር ቦታ ተጠሪ ምንም ዓይነት ህጋዊ መብት ሳይኖረው ከአንድ አመት በፊት ጀምሮ በይዞታዬ ላይ ግንባታ ለማከናወን አጥር ሲያጥር አመልካች ይዞታዬን ለማስከበር ይዞታዬን አትንኩ በማለት የተከላከልኩ ቢሆንም ወቅታዊ ምክንያትን እንደምቹ ሁኔታ በመጠቀም ያለፈቃዴ ይዞታዬ ገብቶ አጥር በማጠር ይዞታዬን ሙሉ በሙሉ በሀይል ቀምቶ 50,000 ካሬ ሜትር ቦታ ይዞብኛል፡፡ አመልካች ይዞታዬ እንዲመልስልኝ ስጠይቅ ብቆይም ምንም ዓይነት መፍትሄ ማግኘት አልቻልኩም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ምንም ዓይነት መብት ሳይኖረው ግብር ምንገብርበት ህጋዊ ይዞታዬን በሀይል ነጥቆ የያዘብኝ መሆኑ ተረጋግጦ ይዞታዬን እንዲመለስ እንዲወሰን በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

በስር ፍ/ቤት ተከሳሽ የነበረዉ የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ የሰጠዉ መልስ ይዘት፡- ለ1ኛ ተጠሪ በሊዝ ዉል የተሰጠው 37,765.10 ካሬ ሜትር ሲሆን ተጨማሪ 6,951 ካሬ ሜትር ሊሰጥ በሂደት ላይ ይገኛል፡፡ ይህም ጠቅላላ ስፋቱ 44,716.1 ካሬ ሜትር ነው፡፡ የመሬት ይዞታዉ ከሊዝ ክፍያ አንፃር ሲታይ የንብረት ግምቱ ከ5 ሚሊዮን ብር በላይ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ዓይቶ የመወሰን ስልጣን የለዉም፡፡ አመልካች በዚህ ክስ የተጠቀመው ተመሳሳይ ማስረጃ በማያያዝ በፌዴራል

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ ችሎት በመ/ቁ. 281928 ክስ አቅርቦ ውድቅ ሆኖበት ይግባኝ የቀረበበት በመሆኑ ክሱ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.5 መሰረት የመጨረሻ ፍርድ ባገኘ ጉዳይ በድጋሚ ያቀረቡት ክስ በመሆኑ ዉድቅ ሊደረግ ይገባል፡፡ አመልካች ወላጅ እናቱ ለግብርና ይዞታ በ1985 ዓ.ም የከፈሉበትን ደረሰኝ ያቀረበ ሲሆን ከዚህ ጊዜ በኋላ የያዙ መሆኑን ማስረጃ አላቀረበም በይዞታው ላይ እስካሉበት ጊዜ ድረስ ይገባኛል ጥያቄ አልቀረበም፡፡ ተጠሪ በዚህ ይዞታ ላይ ካርታ ያወጣው በቀን 03/03/2012 ዓ.ም እና በ26/03/2012 ዓ.ም በመሆኑ አመልካች እያሉ ተጠሪ ባለመብት ሆኗል፡፡ መብት ከኖራቸውም መብታቸው ከ1985 ዓ.ም በኋላ የተቋረጠ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች የመሬት ይገባኛል ጥያቄ ከመሬት ጋር ያላቸው ግንኙነት ከተቋረጠ ከ10 ዓመት በኋላ የቀረበ ክስ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1149 እና 1145 ቀሪ ሆኗል፡፡ አመልካች ከቅን ልቦና ውጪ የሚንቀሳቀሱ ሲሆን ሀሰተኛ ሰነዶች በመጠቀም ተገቢነት የሌለው የክስ አቤቱታ ስላቀረቡ ዉድቅ ሊደረግ ይገባል፡፡

ለተጠሪ ቦሌ ቡልቡላ ወረዳ 12 ውስጥ አራት የመሬት ይዞታዎች በምትክነት የተሰጡኝ ስለሆነ አመልካች ክስ ያቀረበው ከየትኛው የመሬት ይዞታ ላይ እንደሆነ በግልፅ ለይቶ ያላቀረበና ክሱ ግልፅነት የጎደለው በመሆኑ ግልፅ እንዲደረግልን፡፡ አመልካች ክስ ያቀረቡበት ይዞታ ላይ በ15 ዓመት መሬቱ በእጅ አድርጎ ግብር የከፈለበት መሆኑን የሚያመላክት ማስረጃ አላቀረበም፡፡ አመልካች በመሬት ይዞታዉ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብትና ጥቅም ሳይኖራቸዉ ያቀረቡት ክስ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 33 እና 231 መሰረት ውድቅ እንዲደረግ በማለት የጠየቀ ሲሆን የአዲስ አበባ መሬት ማኔጅመንት ቢሮ እና የመሬት ባንክ እና ማስተላለፍ ጽ/ቤት የመሬት ማኔጅመንት ቢሮ እና የመሬት ባንክ ማስተላለፍ ጽ/ቤት እንዲሁም የቦሌ ክ/ከተማ የመሬት ባንክ እና ማስተላለፍ ፅ/ቤት በተከሳሽነት ወደ ክርክሩ እንዲገቡ በመጠየቅ ተከራክሯል፡፡

ከ2ኛ እስከ 11ኛ ተራ ቁጥር የተዘረዘሩት ተጠሪዎች ጣልቃ እንዲገቡ ተደርጎ መልስ የሰጡ ሲሆን፤ የአሁን 3ኛ ተጠሪ የሰጠዉ መልስ ባጭሩ፡- አመልካች ተጠሪ ይዞታዬን በኃይል ነጠቀኝ ከማለት በስተቀር መቼና በምን አግባብ እንደተነጠቀ ያልገለፀ በመሆኑ እንዲገልጽና የይርጋ ክርክር እንድናቀርብ ይደረግልን፡፡ መሬቱ ወደ የመሬት ባንክ የገባ መሆኑን የአዲስ አበባ መሬት ልማት እና ማኔጅመንት ቢሮ የመሬት ባንክና ማስተላለፍ ፅ/ቤት በቀን 16/13/2011 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ አሳውቋል፡፡ ስለሆነም ይህ ቦታ በሊዝ ወደ ተጠሪ በኋላም ወደ 1ኛ ጣልቃ ገብ ከመተላለፉ በፊት በመሬት ባንክ እንጂ በአመልካች እጅ ያልነበረ በመሆኑ ያቀረቡት ክስ በ2 ዓመት ይርጋ ውድቅ እንዲደረግልን፡፡ አመልካች 50,000 ካሬ ሜትር ግምቱ 10,000 (አስር ሺ ብር) ግምት በመስጠት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ከ10 ሚሊየን ብር በላይ የሚያወጣ ንብረት ዋጋውን በማሳነስ ዳኝነት ላለመክፈል ያቀረበውን ክስ በመሆኑ ይዞታው በገለልተኛ ባለሙያ ተገምቶ ተገቢውን ዳኝነት እንዲከፍሉ እና ይህ ፍ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 1234/13 መሰረት ጉዳዩ አይቶ የመወሰን የስረ-ነገር ስልጣን የሌለው በመሆኑ ጉዳዩ የማየት ስልጣን የለኝም በሚል ውድቅ እንዲደረግልን በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ከአማራጭ መልስ ጋር አቅርበዋል፡፡

የአሁን 4ኛ ተጠሪ ባቀረቡት መልስ፡- አመልካች የመፋለም ክስ ያቀረቡት በመሬት ላይ ነው፡፡ በይዞታው ላይ በገንዘባቸው የገነቡት እና ባለቤት የሆኑበት የማይንቀሳቀስ ንብረት ያለ መሆኑን ክሳቸው አይገልፅም፡፡ በሀገራችን ህግ ግለሰቦች የመሬት ባለቤት መሆን ስለማይችሉ እና አመልካቾችም የግል ንብረታቸው ባልሆነ መሬት ላይ የግል ባለሃብትነትን መብት ለማስከበር ታስቦ የተደነገገው የፍ/ሕ/ቁ.1206 በመጥቀስ የመፋለም ክስ ማቅረብ ስለማይችሉ ክሱ የክስ ምክንያት የለውም ተብሎ ያቀረቡት ክስ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.231 መሰረት እንዲዘጋልን፤ አመልካች ክስ ያቀረቡት በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የቀረበ ክስ በመሆኑ ክሱ የቀረበበት ንብረት ለይቶ ለማወቅ የሚያስችሉ ምልክቶች ወይም የወሰን ምልክት መግለፅ አለበት፡፡ አመልካች ተይዞብኛል የሚሉት የይዞታ ወሰን ምልክት ለይተው አልገለፁም ይህ አለመሆኑ በአግባቡ ተረድቼ በበቂ ሁኔታ እንዳልከላከል ከመደረጉም በላይ ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት በሚያስችል ሁኔታ ግልፅ ሆኖ የቀረበ አይደለም፡፡ ስለሆነም ክሱ ግልፅ ሆኖ እንዲቀርብ እንዲታዘዝልን በማለት እንዲሁም የ1ኛ ጣልቃገብ መቃወሚያ በማጠናከር የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ከአማራጭ መልስ ጋር አቅርበው ተከራክረዋል፡፡

የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ የሆነዉ የቦሌ ክ/ከተማ መሬት ልማት አስተዳደር ፅ/ቤት ያቀረበዉ መልስ ይዘት፡- ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ይዞታ ለ1ኛ ተጠሪ በአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ በ15/10/2011 በቁጥር አአ/አ/ፅ//03/30.10/65 በሰጠው ውሳኔ የተላለፈ በመሆኑ በፌደራል አስተዳደር ሥነ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀፅ 49(1) መሰረት ማንኛውም የአስተዳደር ውሳኔ ለማስከለስ የሚቀርብ ክስ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መቅረብ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ በመሆኑም ከዚህ አዋጅ አንፃር ይህ ክስ ሊቀርብ የሚገባው ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 244(2)ሀ መሰረት ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት መዝገቡ እንዲዘጋልን፤ አመልካች 50,000 ካሬ ሜትር ይዞታን ግምቱን 10,000 (አስር ሺ ብር) በማድረግ ያቀረቡት ክስ በመሆኑ በአዲስ አበባ ውስጥ ያለው ይህንን ያህል ስፋት ያለው ይዞታ የተባለውን አነስተኛ ዋጋ ሊኖረው የማይችል ስለሆነ ዋጋውን በማሳነስ ዳኝነት ላለመክፈል

ያቀረበው ክስ በመሆኑ ይዞታውን አመልካች በአካባቢው የመሬት ሊዝ ዋጋ መሰረት በማድረግ ተገቢውን ዳኝነት እንዲከፍሉ እንዲታዘዝልን ወይም መዝገቡ በብይን እንዲዘጋልን፤ አመልካች ክስ ባቀረቡበት ይዞታ ላይ መብት እና ጥቅም እንዳላቸው ሳያረጋግጡ ያቀረቡት ክስ ስለሆነ ክሱ ውድቅ እንዲደረግልን በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ከአማራጭ መልስ ጋር አቅርበዋል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተጠሪዎች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮና መርምሮ፡- አመልካች ባቀረበው ክስ በቀረበበት ይዞታ ላይ ተጠሪ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ያገኙበት በመሆኑ ክሱ በአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2013 መሰረት በአስተዳደር አካሉ ውሳኔ ካገኘ በኋላ በውሳኔው ቅር የተሰኘ አካል የክለሳ ጥያቄ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሚያቀርብ በመሆኑ ይህ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን የለውም በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 245(5) እና 231 (1/ለ) መሰረት ክሱን ውድቅ በማድረግ ብይን ሰጥቷል፡፡ በዚህ ብይን ቅር በመሰኘት የአሁን አመልካች የይግባኝ ቅሬታቸዉን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የሰበር አቤቱታዉም ሊቀርብ የቻለዉ ይህ ብይን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በሚል ነዉ፡፡

አመልካች ግንቦት 14 ቀን 2015 ዓ.ም የተዘጋጀ 4 ገጽ የሰበር አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን መሠረታዊ ይዘቱም በአጭሩ፡- አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያቀረብኩት ክስ በውርስ የተላለፈልኝን ይዞታዬን 1ኛ ተጠሪ ከህግ አግባብ ውጭ ስለያዘብኝ እንዲለቅ በሚል የቀረበ የመፋለም ክስ በመሆኑ ክሱን አይቶ የመወሰን ስልጣን የመደበኛ ፍርድ ቤቶች እንጂ የአስተዳደር አካላት አይደለም፡፡ ከዚህ ጉዳይ ጋር ተያይዞ የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ተከራካሪ በመሆን ሲከራከርበት ቆይቶ አስገዳጅ የህግ ትርጉም በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በኮ/መ/ቁጥር 235053 መጋቢት 29 ቀን 2015 ዓ.ም ተሰጥቶበታል፡፡ በተሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሠረት የቀረበው ክስ የባለቤትነት መብት ተረጋግጦ ውሳኔ እንዲሰጥበት ዳኝነት በተጠየቀበት ጊዜ ካርታ ይሰረዝልኝ ጥያቄ በተጨማሪነት ቢቀርብ እንኳን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ስልጣን አለው በማለት ወስኗል፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፍርድ ቤቱ ስልጣን የለውም ያለው ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 220042 የሰጠዉን የህግ ትርጉም መሠረት በማድረግ ቢሆንም ትርጉሙ በሰ/መ/ቁጥር 235053 በተሰጠው ውሳኔ የተለወጠ በመሆኑ ብይኑ ተገቢ አይደለም፡፡

በአዋጅ ቁጥር 1183/12 አንቀጽ 48 መሰረት ማንኛውም በአስተዳደር ውሳኔ መብቱ የተነካበት ሰው ውሳኔው በፍርድ ቤት እንዲከለስለት አቤቱታ ማቅረብ ይችላል ተብሎ የተጠቀሰው ድንጋጌ በዚህ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ጉዳይ ላይ ተፈፃሚነት የለውም፡፡ ካርታ መስጠት በአዋጅ ቁጥር 1183/12 መንፈስ አስተዳደራዊ ውሳኔ ሊሆን አይችልም፡፡ የስር ፍ/ቤት በፍርድ ሀተታው ካርታው በካቢኔ ውሳኔ ስለተሰራ የአስተዳደር ወሳኔ ነው ያለ ቢሆንም 1ኛ ተጠሪ ካርታው በካቢኔ ውሳኔ የተሰራ መሆኑን ለማሳየት ያቀረበው ማስረጃ የካቢኔ ውሳኔ ለማስተላለፍ ሊሟሉ የሚገቡትን ቅድመ ሁኔታዎች አሟልቶ የቀረበበት አይደለም፡፡ የካቢኔ አባላት ውሳኔ ነው ቢባል እንኳን የተላለፈው ውሳኔ ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነው አመልካች ተይዞብኛል ያልኩት መሬት ለ1ኛ ተጠሪ እንዲሰጥ የተላለፈ ውሳኔ አይደለም፡፡ በመሆኑም የካቢኔ ውሳኔ ነው የተባለው ስብሰባ ላይ አመልካች ይዞታዬ ነው ያልኩት መሬት ለ1ኛ ተጠሪ እንዲሰጥ ውሳኔ ባልተላለፈበት ሁኔታ የካቢኔ ውሳኔው እንዲሰረዝ አቤቱታ ለአስተዳደር አካሉ ቀርቦ በአስተዳደር አካሉ በሚሠጠው ውሳኔ ለማስከለስ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቤቱታ ማቅረብ አንችልም፡፡ በመሆኑም የስር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ካርታ መሰጠቱ በአዋጅ ቁጥር 1183/12 መንፈስ የአስተዳደር ውሳኔ ባልሆነበት ሁኔታ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንደ ማስረጃ በመቅረቡ ብቻ ካርታው እንደ አንድ የሰነድ ማስረጃ ተመዝኖ ውሳኔ የሚሰጥበት ሆኖ ሳለ እንዲሁም ተላለፈ በተባለው የካቢኔ ውሳኔ ይዞታዬ ለ1ኛ ተጠሪ እንዲሰጥ ውሳኔ ባልተላለፈበት ሁኔታ ካርታ ይዞታው ላይ በመሰጠቱ ብቻ የአስተዳደር ውሳኔ መሆኑን ያሳያል በማለት ፍ/ቤት ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ስልጣን የለውም ተብሎ የተሰጠዉ ውሳኔ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል፡፡ በስር ፍ/ቤት አመልካች ያቀረብኩት ክስ ካርታ እንዲመክን አይደለም፡፡

የስር ፍ/ቤት በውሳኔው ላይ የጠቀሰው የሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ያቀረብነው ክስ ጋር ተያያዥነት የላቸውም፡፡ ፍ/ቤቱ የመፋለም ክሱን አይቶ ውሳኔ ቢሰጥበት የሚሰጠው ውሳኔ የአስተዳደር ውሳኔን ለማስከለስ የሚቀርብ አቤቱታ ላይ ከሚሰጠው ውሳኔ ጋር የሚለያይ ከሆነ ውሳኔውም መፈጸም የማይቻል ይሆናል በማለት የፍርድ ሀተታው ላይ የገለጸው ሀተታ ፍ/ቤቱ የቀረበለትን የመፋለም ክስ አይቶ የመወሰን ስልጣን ያለው መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ፍ/ቤቱ የመፋለም ክሱን አይቶ የመወሰን ስልጣን ያለው መሆኑን ካመነበት ደግሞ ከጠየቅነው ዳኝነት ውስጥ ፍ/ቤቱ ለመወሰን ስልጣን የተሰጠውን በመወሰን ከተጠየቀው ዳኝነት ፍ/ቤት የመወሰን ስልጣን የለውም በማለት የሚያምንበትን ውድቅ ማድረግ እያለበት በህጉ በመደበኛ ፍ/ቤት ስልጣን ስር የሚወድቀውን የመፋለም ክስ ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል፤ ውሳኔው ተሽሮ የስር ፍ/ቤት የቀረበለት የፍሬ ነገር ክርክር ላይ አከራክሮ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ለስር ፍርድ ቤት እንዲመለስለት እንዲወሰ የሚጠይቅ ነዉ፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች የዳኝነት ጥያቄ ይዞታን በማስለቀቅና ለመረከብ የቀረበ የመፋለም ክስ ሲሆን የከሰሱትም 2ኛ ተጠሪ የሆነውን የአስተዳደር አካልን ሳይሆን ይዞታችን አላግባብ ያዘብን የሚሉትን 1ኛ ተጠሪ ማህበርን መሆኑን፤ 2ኛ ተጠሪ ወደ ክርክሩ እንዲገባ የተደረገዉ በፍርድ ቤት ትእዛዝ ጉዳይ ይመለከተኛል በሚል መሆኑን እንዲሁም ሌሎች ተጠሪዎች በጣልቃ ገብነት ወደ ክርክሩ መግባታቸዉን የሚያሳይ ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩ በፌደራል አስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 መሰረት በዳኝነት ክለሳ ነው አቤቱታው መቅረብ ያለበት በሚል መሰረዙ ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 229531 ላይ ከሰጠው አስገዳጅ ትርጉም አንፃር ተገቢነቱን ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ በሰበር ችሎት እንዲታይ የተደረገ ነዉ፡፡

1ኛ ተጠሪ በሰጡት መልስ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ጸንተው ባሉበት በአዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 49 እና 52 መሰረት ፍርድ ቤቶች የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1195 እና 1196 በመጥቀስ የመፋለም ክርክር ማየት አይችሉም፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1195 እና 1196 የተመለከቱት ድንጋጌዎች በአዋጅ ቁጥር 818/06 አንቀጽ 43 መሰረት የይዞታ ምዝገባ እና የሊዝ ውል እስካልተሰረዘ ድረስ ክርክር ለማንሳት ሌላ ግለሰብ አይችልም፡፡ የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 229531 ፍርድ የሰጠው ከዚህ ጉዳይ ጋር የስረ-ነገር፣ የጭብጥ እና የህግ ክርክር ልዩነት ያለው ሲሆን የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት በግልጽ የተመለከተ የህግ ድንጋጌን በትርጉም ሰበብ ለመለወጥ ወይም ለማሻሻል አይችልም፡፡ ስለዚህ ይህ ጉዳይ የመፋለም ባልሆነበት እና ለጉዳዩ ተገቢነት የሌለው የሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ተጠቅሶ ያስቀርባል የተባለው ጉዳዩ ተገቢነት የሌለው ስለሆነ አቤቱታው እንዲሰረዝ፤ ማህበሩ አከራካሪ የመሬት ይዞታ ላይ የሊዝ ውል የፈረመ ሲሆን በህጉ በተመለከተው መሰረት የሊዝ መብቱን ከ3ኛ እስከ 11ኛ ተጠሪዎች በሰነዶች ማረጋገጫ እና ምዝገባ አገልግሎት በተደረጉ ውሎች ማስተላለፉ ግልጽ ነው፡፡ እነዚህ የሊዝ ውሎች እና የሊዝ መብት ማስተላለፍ ስምምነቶች በአዋጅ ቁጥር 721/04 አንቀጽ 25 መሰረት ሊቋረጡ የሚችሉት በአስተዳደር መስሪያ ቤት እንጂ በፍርድ ቤት አይደለም፡፡ አስተዳደራዊ ውሳኔ የሚፈልጉ ነገሮችን በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 49 እና 52 መሰረት ለአስተዳደር መስሪያ ቤቱ አቤቱታ የሚቀርብበት እንጂ በቀጥታ ፍርድ ቤት ክስ የሚቀርብበት ባለመሆኑ በሥር ፍ/ቤቶች የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

2ኛ ተጠሪ የሰጡት መልስ ይዘት፡- አመልካች የሥር ፍ/ቤት ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ስልጣን ያለው የአስተዳደር አካል ነው እንጂ ይህ ፍ/ቤት አይደለም በማለት የሰጠው ውሳኔ እኛ የጠየቅነው

የመፋለም ዳኝነት ጥያቄ የፍ/ቤቱ ስልጣን በመሆኑ የፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 235053 ከሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም አንጻር መሰረታዊ የህግ ጥሰት የተፈፀመበት ነው ይበሉ እንጂ ከጅምሩም የፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 235053 ውሳኔ የሰጠው መጋቢት 29 ቀን 2015 ዓ.ም ሲሆን ይግባኝ ባይ ቅር የተሰኙበት ውሳኔ የተሰጠው ደግሞ መጋቢት 20 ቀን 2015 ዓ.ም በመሆኑ የጠቀሱት የሰበር መዝገብ ቁጥር ውሳኔ በተሰጠ ሰአት ያልነበረ በመሆኑ ተግባራዊ የሚደረግበት የህግ አግባብ የለም፡፡ አመልካች ፍ/ቤቱ የመፋለም የዳኝነት ጥያቄን ለማየት ስልጣኑ እንደሆነ አምኖ እያለ በዚሁ ላይ ውሳኔ መስጠት ሲችል ሁለት አይነት ውሳኔ ቢሰጥ ለማስፈፀም ያስቸግራል በሚል መዝገቡን መዝጋቱ መሰረታዊ የህግ ጥሰት የተፈፀመበት ነው ቢሉም የስር ፍ/ቤት ውሳኔውን የሠጠው አመልካች ባሉበት አግባብ ሳይሆን የፌዴራል አስተዳደር ስነ-ስርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 በደነገገው መሰረት እና በካቢኔ ውሳኔ የተሰጠ ህጋዊ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ፀንቶ ባለበት ወይም ይህ ካርታ ሳይመክን ምንአልባትም የሚቃረን ውሳኔ ቢሰጥ የመፋለም የዳኝነት ጥያቄውን ለመወሰን እና ለማስፈፀም የማይቻል መሆኑን በመግለጽ የሰጠው ውሳኔ በመሆኑ የሚሻርበት የህግ አግባብ የለም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

ከ3ኛ እስከ 10ኛ ያሉት ተጠሪዎች በበኩላቸዉ በሰጡት መልስ- በስር ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር የአሁን 2ኛ ተጠሪ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ጣልቃ እንዲገባ ተደርጎ የክርክሩ አካል ሆኗል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ካለበት ነጥብ አንጻር የአመልካች ክርክር ተቀባነት ሊያገኝ ይችል የነበረው ክርክሩ በግለሰቦች መካከል ብቻ ቢሆን የነበረ ሲሆን አመልካች ከአስተዳደሩ ጋር ባላቸው ክርክር የመፋለም ክርክር ሊያቀርቡ አይችሉም፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካብኔ የሰጠውን ውሳኔ መሰረት በማድረግ የአዲስ አበባ ከተማ መሬት ልማት አስተዳደር እና የቦሌ ክፍለ ከተማ መሬት ልማት አስተዳደር ተቀብለው ለተጠሪዎች የተሰጠ የባለቤትን ማረጋገጫ በተመለከተ የሚቀርብ ክርክር የመፋለም ክርክር ሳይሆን አዋጅ ቁጥር 1183/12 መሰረት የሚታይ አስተዳደራዊ ጉዳይ በመሆኑ በፍ/ቤቱ የስልጣን ክልል ስር የሚወድቅ ባለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ብይን መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክረዋል፡፡

11ኛ ተጠሪ በበኩሉ በሰጠው መልስ አመልካች በይዞታው ላይ በገንዘባቸው የገነቡትና ባለቤት የሆኑበት የማይንቀሳቀስ ንብረት ያለ መሆኑን ክሳቸው አይገልጽም፡፡ አሁን በሀገራችን ባለው የህግ ሥርዓት ግለሰቦች የመሬት ባለቤት መሆን ስለማይችሉና አመልካቾችም የግል ንብረታቸው ባልሆነ መሬት ላይ የግል ባህብትነትን መብት ለማስከበር ታስቦ የተደነገገውን የፍ/ሕግ ቁጥር 1206 ድንጋጌን በመጥቀስ የመፋለም ክስ ለማቅረብ ስለማይችሉ አመልካቾች የክሱን አርእስት የመፋለም

ክስ ብለው ስለሰየሙ ብቻ ክሱ የመፋለም ክስ ነው ሊባል አይችልም፡፡ ለ1ኛ ተጠሪ ካርታ የተሰጠውም በካቢኔው ውሳኔ መሰረት ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤት አመልካች ካርታው የተሰጠበትን አስተዳደራዊ ውሳኔ ካሰረዙ በኂላ የመፋለም ክስ የማቅረብ መብታቸውን ጠብቆ አሁን ክሱ በቀረበበት ሁኔታ ግን ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ውሳኔ ትክክለኛ የህግ ትርጉም የተሰጠበት ውሳኔ እንጂ የሚነቀፍ አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸዉን በሚያጠናክር መልኩ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን እኛም አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡ የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥና ግራ ቀኙ ካደረጉት ክርክር አንጻር መርምረን እንደተረዳነዉ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሻዉ ነጥብ፡- የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ይዞታን በማስለቀቅና ለመረከብ የቀረበ የመፋለም ክስ ሲሆን የከሰሱትም 2ኛ ተጠሪ የሆነውን የአስተዳደር አካል ሳይሆን ይዞታችን ለአግባብ ያዘብኝ የሚሉትን 1ኛ ተጠሪ ማህበርን መሆኑን፤ 2ኛ ተጠሪ ወደ ክርክሩ እንዲገባ የተደረገዉ በፍርድ ቤት ትእዛዝ ጉዳይ ይመለከተኛል በሚል መሆኑን እንዲሁም ሌሎች ተጠሪዎች በጣልቃ ገብነት ወደ ክርክሩ መግባታቸዉን የሚያሳይ ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩ በፌዴራል አስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 መሰረት በዳኝነት ክለሳ ነው አቤቱታው መቅረብ ያለበት እንጂ በቀጥታ ክስ አይደለም፤ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለኝም በሚል ክሱን ዉድቅ በማድረግ የሰጠዉ ብይን ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 229531 ላይ ከሰጠው አስገዳጅ ትርጉም አንፃር መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነዉ፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ዳኝነት የጠየቁት 50,000 ካሬ ሜትር ስፋት ያለዉን የመሬት ይዞታቸዉን 1ኛ ተጠሪ በኃይል የያዘባቸዉ መሆኑን ገልጸዉ ይዞታቸዉን ለቅቆ እንዲያስረክባቸዉ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ ወደ ክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ከተደረገ በኃላ ክርክር ያስነሳዉ ይዞታ ከይገባኛል ጥያቄ ነጻ መሆኑ ተረጋግጦና ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ ተደርጎ የካብኔ ዉሳኔን ጨምሮ የተለያዩ የአስተዳደር ተቋማት ዉሳኔ ተሰጥቶበት በሊዝ ዉል ለ1ኛ ተጠሪ እንዲተላለፍ ተደርጎና የይዞታ ማረጋገጫ ተሠርቶ የተሰጠበት በመሆኑ በክለሳ እንጂ በቀጥታ ለመደበኛ ፍ/ቤት ክስ የሚቀርብበት አይደለም የሚል መከራከሪያ አቅርቧል፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም በመቃወሚያዉ ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮና መርምሮ የክ/ከተማዉ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት በአስተዳደራዊ ዉሳኔ ካርታ ሰርቶ ለ1ኛ ተጠሪ የሰጠ በመሆኑ ይህ ካርታ ካርታዉን ሰርቶ

የሰጠዉ አካል እንዲሰርዘዉ አመልካች ጥያቄ አቅርቦ በአዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 43፣ 44 እና ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 220042 በሰጠዉ ትርጉም መሰረት አስተዳደራዊ ዉሳኔ እንዲሰጥበት በማድረግ፤ በዉሳኔዉ ቅሬታ ካላቸዉ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የክለሳ ጥያቄ ከሚያቀርቡ በቀር ሂደቱን ሳይጠብቁ ያቀረቡት ክስ ነዉ በማለት ዉድቅ በማድረግ ብይን ሰጥቷል። የዚህን ብይን ተገቢነት ቀጥለን እንመልከት።

በመሠረቱ በፌዴራል አስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 56(2) እና (3) መሠረት በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የአስተዳደር ውሳኔ የሚከለሰው አስተዳደር መሥሪያ ቤቱ በሕግ ከተሰጠው ሥልጣን ወሰን በማለፍ የወሰነዉ ዉሳኔ ከሆነ ወይም በሕጉ የተመለከቱ ሂደቶችን ሳይከተል የወሰነ ከሆነ ነው። የአዋጁ አንቀጽ 2(3) ደግሞ አስተዳደራዊ ዉሳኔ ማለት መመሪያ ማዉጣትን ሳይጨምር የአስተዳደር ተቋም በዕለት ተዕለት ተግባሩ በሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ የሚሰጠዉ የአስተዳደር ዉሳኔ ነዉ በማለት ትርጉም ሰጥቶበታል። ከዚህ መገንዘብ የሚቻለዉ የክለሳ ጥያቄ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሚቀርበዉ የአስተዳደር አካሉ በራሱ ተነሳሽነት ወይም አቤቱታ ቀርቦለት በዕለት ተዕለት ተግባሩ የሰጠዉ አስተዳደራዊ ዉሳኔ ሲኖርና ዉሳኔዉ መብቱን ወይም ጥቅሙን የነካበት ሰዉ ሂደቱን ጠብቆ የክለሳ ጥያቄ የሚያቀርብበት ነዉ። በርግጥ ሰበር ችሎተ በሰ/መ/ቁ 220042 በሰጠዉ ትርጉም የዳኝነት ጥያቄዉ የካርታ ይምከንልኝ ሲሆን የአስተዳደር አካሉ የዕለት ዕለት ሥራን የሚመለከት በመሆኑ በቅድሚያ ለአስተዳደር አካሉ ጥያቄዉ ቀርቦ በሚሰጠዉ ዉሳኔ ቅሬታ ያለዉ ወገን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የክለሳ ጥያቄ ያቀርባል እንጂ በቀጥታ ክስ ሊቀርብ እንደማይገባዉ ትርጉም ተሰጥቶበታል።

በሌላ በኩል ይዞታ ያለአግባብ ተያዘብኝ፤ ይዞታዬ ይለቀቅልኝ በሚል ወይም የመፋለም የዳኝነት ጥያቄ ቀርቦ በግለሰቦች መካከል የሚደረግን ክርክር የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የተሰጠበትም ሆነ ካርታ ያልተሰጠበት ቢሆንም ክርክርና ማስረጃዉ ተመዝኖ በመደበኛ ፍ/ቤት በቀጥታ ዉሳኔ የሚሰጥበት ነዉ። ይዞታዉ የማን ነዉ ወይም በይዞታዉ ላይ የተሻለ መብት ያለዉ ማን ነዉ የሚል ጭብጥ ተይዞ ባለይዞታ ነን በሚሉ ሰዎች መካከል የሚደረግ ክርክር በቀጥታ ለመደበኛ ፍ/ቤት ክስ የሚቀርብበት እንጂ የግድ አስተዳደራዊ ዉሳኔ ተሰጥቶበት በክለሳ ለፍ/ቤት መቅረብ አለበት የሚባል አይደለም። የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 220582 ላይ ካርታ እንዲመክን የቀረበው ክስ በዳኝነት ክለሳ የሚታይ ነው በማለት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 መሠረት ተደርጎ የተወሰነ ከመሆኑ ባሻገር የመጨረሻ ዳኝነቱ ተመሳሳይ የሆነ ነገር ግን እንደ ክስ አቀራረብና ይዘት የሚነሳው ጭብጥ የተለያየ በሆነ ጊዜ ሁሉም ክስ በአዋጅ ቁጥር

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

1183/2012 መሠረት ብቻ እንዲታይ አስገዳጅ ሆኖ የተሰጠ ትርጉም አለመሆኑንና ይዞታው የማን ነው የሚል ጭብጥ ተይዞ የሚወሰን ጉዳይ መቅረብና መታየት ያለበት በቀጥታ በመደበኛ ፍ/ቤት መሆኑን የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 229531 እና በሌሎች መዛግብት ገዥ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለዉ ዋናዉ የዳኝነት ጥያቄ ያለአግባብ የተያዘብኝ ይዞታ ይለቀቅልኝ የሚል የዳኝነት ጥያቄ ሲቀርብ ይዞታዉ የማን ነዉ? ወይም በይዞታዉ ላይ የተሻለ መብት ያለዉ ማን ነዉ? ተብሎ ጭብጥ ተይዞ ዉሳኔ የሚሰጥበት ጉዳይ ላይ የተሰጠ ካርታ ቢኖርም እንኳ ካርታዉ እንደ አንድ ማስረጃ ከሚመዘን በቀር የይዞታዉ ክርክር ቆሞ ካርታዉ እንዲመክን ለአስተዳደር አካሉ ጥያቄ ቀርቦ ካርታዉ ካልተሰረዘ በቀር ይዞታዉን የማስለቀቅ ክስ ለመደበኛ ፍ/ቤት በቀጥታ ሊቀርብ አይገባም ሊባል የሚችል አለመሆኑን ነዉ፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች በስር ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ዳኝነት የጠየቁት ያለአግባብ በሀይል የተያዘባቸዉ ይዞታ እንዲለቀቅላቸዉ ወይም የመፋለም ክስ መሆኑን የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ቢያረጋግጥም ለ1ኛ ተጠሪ ይዞታዉ የተላለፈዉ በካቢኔ ዉሳኔ ሆኖ ካርታ የተሠራ በመሆኑ ካርታዉ ካልመከነ ይዞታዉ የከሳሹ ነዉ ተብሎ ቢወሰን እንኳ ፍርዱ ሊፈጸም የማይችል በመሆኑ ቅድሚያ ካርታ ሊመክን ይገባል የሚለዉን ተያያዥ ጥያቄን የሚያስነሳ በመሆኑ ካርታ ሊመክን ይገባል ወይስ አይገባም የሚለዉን ደግሞ በቀጥታ ዓይቶ መወሰን የአስተዳደር አካሉ ስልጣን ነዉ፡፡ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን በቀጥታ የመወሰን ስልጣን የለዉም፤ አመልካች በይዞታዉ ላይ የተሰጠዉን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በአስተዳደር አካሉ ዉሳኔ ካስሰረዘ በኃላ የመፋለም ክሱን የማቅረብ መብታቸዉን ጠብቆ የአመልካችን ክስ ዉድቅ አድርጎታል፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤት ባቀረበዉ ክስ ለ1ኛ ተጠሪ የተሰጠዉ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንዲመክን ያቀረበዉ የዳኝነት ጥያቄ አለመኖሩ አከራካሪ አይደለም፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 182(2) መሠረት ፍርድ ቤት ክርክርን መወሰን የሚገባዉ ከቀረበዉ የዳኝነት ጥያቄ አኳያ እንጂ ዳኝነት ባልተጠየቀበት አንደኛዉ ወገን በቅድሚያ ሌላ የዳኝነት ጥያቄ ጠይቆ ካላስወሰነ በቀር ዳኝነቱ ሊታይለት አይገባም ሊባል አይገባም፡፡ የስር ፍ/ቤት ግራ ቀኝ በሌሎች ነጥቦች ላይ አከራክሮ ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ መስጠት ሲችል በመፋለም ክሱ ወይም የባለይዞታነት ክርክሩ ላይ ዉሳኔ ከመሰጠቱ በፊት በቅድሚያ ካርታዉ መምከን አለበት የሚል እሳቤ በመያዝ፤ በጉዳዩ ላይ አስተዳደራዊ ዉሳኔ ተሰጥቶበት ካርታ እንዲመክን ካልተደረገ በቀር ዉሳኔ መስጠት አይቻልም በሚል ለተያዘዉ ጉዳይ ቀጥተኛ አግባብነት የሌለዉን ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 220042 የሰጠዉን ትርጉም መሠረት በማድረግ የአመልካችን ክስ ዉድቅ ማድረጉ ተገቢ አይደለም፡፡

ለጉዳዩ ቀጥተኛ አግባብነት ያለዉ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 229531 በሰጠዉ ገዥ ትርጉም መሠረት የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ይዞታቸዉ ያለአግባብ በ1ኛ ተጠሪ ተይዞብኛል፤ ይለቀቅልኝ የሚል እንደመሆኑ መጠን ጣልቃ-እንዲገቡ የተደረጉትን ሌሎች ተጠሪዎች ጭምር ባካሏቸዉ የክርክር ነጥቦች ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ ተገቢዉን መወሰን ሲችል ጉዳዩን የማዩት ስልጣን የለኝም በማለት የአመልካችን ክስ ዉድቅ በማድረግ የሰጠዉ ብይን ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡ ይግባኝ ሰሚዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህን ስህተት ማረም ሲገባዉ ብይንኑ በትዕዛዝ ማጽናቱ ተገቢ አይደለም፡፡ ስለሆነም የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ያለአግባብ የተያዘብኝ ይዞታ ይለቀቅልኝ የሚል በመሆኑና በቀጥታ ለስር ፍ/ቤት መቅረቡ ተገቢ በመሆኑ ብይኑ ተሽሮ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የዘጋዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ በሌሎች የክርክር ነጥቦች ላይ ተገቢዉን ብይን ወይም ዉሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩ ሊመለስለት የሚገባዉ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሲጠቃለል የስር ፍ/ቤት ካርታ እንዲመክን የቀረበለት የዳኝነት ጥያቄ በሌለበት የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ለማየት ፍ/ቤቱ ስልጣን የለዉም በማለት የሰጠዉ ብይን የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ፤ የፌዴራል አስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 56(2) እና (3)፤ ሰበር ችሎቱ በሰ/መ/ቁ 229531 እና በሌሎች መዛግብት የሰጣቸዉን ገዥ ትርጉሞች ያላገናዘበ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ውሳኔ</u>**

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 128554 መጋቢት 20 ቀን 2015 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 306960 ሰኔ 22 ቀን 2015 ዓ.ም በተሰጠ ብይን የጸናዉ ብይን በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1/ለ) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የዘጋዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው አግባብ በሌሎች የክርክር ነጥቦች ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ ተገቢዉን ብይን ወይም ዉሳኔ ይሰጥበት ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341(1) እና በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(2) መሠረት ጉዳዩ ይመለስለት ተብሎ ተወስኗል፡፡ ይጻፍ፡፡
3. በዚህ መዝገብ ጥር 24 ቀን 2016 ዓ.ም የተሰጠዉ የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ም

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መዝገብ ቁጥር 252225

ጥቅምት 06 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች፡- ወ/ሮ መሰሉ ሽመልስ } vC

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሸዋዬ ገ/ማርያም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ጉዳዩ የውርስ ንብረት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክሱ በቀረበበት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ድሬደዋ ምድብ ችሎት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ አመልካች ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- የሟች አባታቸው አቶ ሽመልስ ገ/ማርያም አባት የሆኑት ሟች አያታቸው ሃምሳ አለቃ ገ/ማርያም ዘለለው ከሟች ወ/ሮ አየለች ኃይሌ ገመዳ ጋር ትዳር መስርተው ሲኖሩ በድሬደዋ ከተማ ቀበሌ 02 ውስጥ ቁጥሩ 6469 የሆነ በሟች ወ/ሮ አየለች ኃይሌ ገመዳ ስም የተመዘገበ ቤት ያፈሩ ሲሆን ፤ ሟች ሃምሳ አለቃ ገ/ማርያም ዘለለው ለሟች አቶ ሽመልስ ገ/ማርያም ፈቅደውላቸው በይዞታው ላይ አንድ ክፍል ቤት ሰርተውና ሟች አባታቸው ሃምሳ አለቃ ገ/ማርያም ዘለለውን ወርሰው ሟች አቶ ሽመልስ ገ/ማርያም በውርስ ሀብቱ ላይ ሲኖሩ ቆይተው አመልካች የስድስት ወር ህፃን እያሉ ጥር 11

ማስታወሻ፡ - ይህ የ ሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነ ድ ለ ጥና ትና ምርምር ሥራ ወይም ለ ግ ን ዛ ቤ እ ን ጂ ለ ፍር ድ አ ፈ ጻ ጸ ም ዓ ላ ማ አ ያ ገ ለ ግ ል ም!

ቀን 1986 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ መሆኑን፤ የሟች ሃምሳ አለቃ ገ/ማርያም ዘለለው ባለቤት የነበሩት ወ/ሮ አየለች ኃይሌ ገመዳ በቤቱ ውስጥ ይኖሩ የነበረው እንደእናት ስለነበረ በማክበር የውርስ ድርሻቸውን ያልጠየቁ መሆኑን፤ ተጠሪ ንብረቱን በስምምነት እንካፈላለን ሲሉ ቆይተው ለብቻቸው ውርስ በማጣራት ካርታ በስማቸው እንዳወጡ ጠቅሰው የውርስ ሀብት የሆነው የቤት ቁጥር 6469 በካርታ ቁጥር 17705 የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተመዘገበው ቤት እና የኪራዩን ግማሽ ድርሻቸውን እንዲያካፍሏቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መልስ አመልካች የሟች አባታቸውንም ሆነ የሟች አያቸውን ተተኪ ወራሽነት ስላላረጋገጡ የውርስ ንብረት ሊጠይቁ አይገባም፡፡ አመልካች በ3 ዓመት ውስጥ ወራሽነታቸውን ስላላረጋገጡና ንብረቱም ከተያዘ 15 ዓ.ም ስላለፈው ያቀረቡት ክስ በይርጋ ይቋረጣል ፤ አስቀድሞ የነበረው ቤት በልማት ምክንያት ስለፈረሰ የክስ ምክንያቱ መቋረጡን ፤ አመልካች ክስ ለማቅረብ መብትና ጥቅም የላቸውም የሚሉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን በፍሬ ነገር መልሳቸውም ሟች ሃምሳ አለቃ ገ/ማርያም ዘለለው ከሟች ወ/ሮ አየለች ኃይሌ ገመዳ ጋር በትደር ተሳስረው ሲኖሩ የነበራቸው በድሬደዋ ከተማ ቀበሌ 02 ውስጥ የሚገኘው ቁጥሩ 494 የሖነ ካርታ ያልነበረው የጭቃ ቤት ሟች ሃምሳ አለቃ ገ/ማርያም ዘለለው ለሟች ወ/ሮ አየለች ኃይሌ ገመዳ በኑዛዜ አስተላልፈው ሟች ወ/ሮ አየለች ኃይሌ ገመዳም ለ21 ዓመታት ይሕን ቤት የግላቸው አድርገው ሲያስተዳድሩት ቆይተው መንገድ ስለወጣበት በ1977 ዓ.ም ሙሉ በሙሉ ፈርሶ ለሟች ወ/ሮ አየለች ኃይሌ ገመዳ ባዶ ቦታ ተሰጥቷቸው በተጠሪ እና ባለቤታቸው እንዲሁም በሌሎች ሰዎች እገዛ የተሰራውን አዲሱን የቤት ቁጥር 6469 ሟች ወ/ሮ አየለች ኃይሌ ገመዳ ለተጠሪ ተናዘው ቤቱ ለ7(ሰባት) ዓመት በእጃቸው መቆየቱን ገልፀው የአመልካች አባት በጠና ታመው ለ3(ሶስት) ወራት በቀድሞ ቤት ከመቆየታቸው ውጪ የሰሩት ቤት ካለመኖሩም በላይ ቀድሞ የነበረው ቤት በ1977 ዓ.ም ፈርሶ አሁን ያለው ቤት ስለተሰራ በክሱ ላይ የተመለከተው ቤት ተጠሪ ከሚኖሩበት ቤት ጋር አይገናኝም የሚል የፍሬ ነገር ክርክር አቅርበዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም በተጠሪ የቀረበውን መቃወሚያ በተመለከተ መጋቢት 23 ቀን 2014 ዓ.ም በሰጠው ብይን አመልካች የሚጠይቁት የሟች አያታቸው ሃምሳ አለቃ ገ/ማርያም ዘለለው ትተው ያለፉትን የውርስ ሀብት ሲሆን ሟች አያታቸው ሃምሳ አለቃ ገ/ማርያም ዘለለው ሰኔ 29 ቀን 1977 ዓ.ም ከሞቱ በኋላ የአመልካች አባት የሖኑት አቶ ሽመልስ ገ/ማሪም ደግሞ ዘጠኝ ዓመት ከስድስት ወር ቆይተው የሟች አባታቸውን ውርስ ሳይጠይቁ ጥር 11 ቀን 1986 ዓ.ም ስሞቱ አመልካች የ6(ስድስት ወር) ሕፃን እንደነበሩ ያቀረቡት ክርክር በተጠሪም ስላልተካደ አመልካች 18(አሥራ ስምንት) ዓመት ከሞላቸው ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ ያለው ጊዜ ሲቆጠር ዘጠኝ ዓመት ከሁለት ወር እንዲሁም ሃምሳ አለቃ ገ/ማርያም ዘለለው ከሞቱበት ከሰኔ 29 ቀን 1977 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ ከ35 ዓመት በኋላ ያቀረቡት ክስ በይርጋ ቀር ነው በማለት በሰጠው ብይን አመልካች ቅር ተሰኝተው ያቀረቡትን የይግባኝ አቤቱታ የተመለከተው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ አቤቱታው ያስቀርባል በማለት ግራ ቀኙን

አከራክሮ በሰጠው ውሳኔ አመልካች የጠየቁት ውርስ የሟች አያታቸው ሃምሳ አለቃ ገ/ማርያም ዘለለውን ሳይሆን ጥር 11 ቀን 1986 ዓ.ም የሞቱትን የሟች አባታቸው አቶ ሽመልስ ገ/ማሪምን ውርስ በመሆኑና አመልካች አባታቸው ሲሞቱ የ6(ስድስት) ወር ሕፃን እንደነበሩ ያቀረቡት ክርክር በተጠሪም ስላልተካደ አመልካች በመብታቸው መሥራት ከቻሉበት (አካለ መጠን ከደረሱበት) ጊዜ አንስቶ ሲቆጥር 10(አሥር) ዓመት ስለማይሞላ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረቡት ክስ በይርጋ ይታገዳል በማለት የሰጠው ብይን አግባብነት የለውም፡፡ የውርስ ሀብት የሆነው ቤት በ1977 ዓ.ም በወጣው የመንገድ ሽንሽና ሙሉ በሙሉ ፈርሶ በሬጉላራይዜሽን ክርክር የቀረበበትን ይዞታ ተጠሪ አግኝተው ስመሀብቱ መዞሩን ከቀረቡት የሰነድ ማስረጃዎች፤ እንዲሁም ከድሬደዋ አስተዳደር ቀበሌ 03 ጥር 20 ቀን 2014 ዓ.ም ከቀረበው የሰነድ ማስረጃ ማረጋገጡን ጠቅሶ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ንብረት በተጠሪ ስም የተመዘገበ በመሆኑና የውርስ ሀብት ለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ ባለመኖሩ አመልካች ሊወርሱ የሚችሉት ንብረት ወይም ከሟች አባታቸው ሊተላለፍላቸው የሚችል መብት ለመኖሩ ማስረጃ አልቀረበም በሚል በውጤት ደረጃ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ብይን በማጽናት ወስኗል፡፡

የሰበር ቅሬታው የቀረበው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ብይን በውጤት ደረጃ በማጽናት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል በሰበር ሰሚ ችሎቱ ለማሳረም ሆኖ የሰበር ቅሬታው በአጭሩ፡- አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት የሟች አባቴ አቶ ሽመልስ ገ/ማርያም መሆኑን የሚያስረዱ የሰው ምስክር የቆጠርኩ ሲሆን የሰነድ ማስረጃም ቀርቦ እያለ እነዚህ ማስረጃዎች ሳይታዩ እና እንዲቀርቡ ሳይደረግ ውሳኔ መሰጠቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት መሆኑን፤ አመልካች ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቤቱታ ያቀረብኩት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክሱ በይርጋ የታገደ ነው ሲል በሰጠው ብይን ላይ ቢሆንም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ግን ከይግባኝ አቤቱታው አድማስ በመውጣት በሥር ፍርድ ቤት ያልቀረበን ክርክር መሠረት አድርጎ አከራካሪው ንብረት በሟች ስም ስላልተመዘገበ የሟች የውርስ ሀብት ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ የለም በማለት ውሳኔ መስጠቱ ሥነ ሥርዓታዊ አይደለም፡፡ የስር ፍርድ ቤት ይርጋውን ለመቁጠር መነሻ ያደረገው ኑዛዜ በእጄ የጨበጥኩት በእግሬ የረገጥኩትን ሁሉ አውርሻለሁኝ የሚለውን ድፍን ያለ ኑዛዜ ተወላጅን የነቀለ ውጤት አልባ ሆኖእያለ ኑዛዜው አከራካሪውን ቤት ይመለከታል በማለት የሰጠው ውሳኔ ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡

በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 6/1 መሠረት ለሰበር ሰሚው ችሎቱ የተመራው አቤቱታ በሰበር ሰሚ ችሎቱ ተመርምሮ የይግባኝ አቤቱታው ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቀረበው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በይርጋ መቃወሚያ ላይ የሰጠውን ብይን በመቃወም በመሆኑ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይርጋ መቃወሚያው

ተቀባይነት የለውም ካለ በሥረ-ነገሩ ላይ ክርክር እንዲሰማና በማስረጃ ተጣርቶ እንዲወሰን በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 341/1 መሠረት ወደ ሥር ፍርድ ቤት ተመልሶ በሥረ-ነገሩ ላይ ክርክር ሳይደረግ የሥረ-ነገር ጭብጥ ይዞ መወሰኑ የተከራካሪዎች የመደመጥ መብት መከበር አለመከበሩን ፣ የክርክር አመራር ሥርዓቱን ተገቢነት ለመመርመር ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ ተከታዩን መልስ ሰጥቷል፡፡ የአመልካች አባት ቤት አልሰሩም እንጅ ሰርተዋል ቢባል እንኳን አመልካች የውርስ ሀብት ነው በማለት የጠየቁት ቤት በ1997 ዓ.ም መንገድ ወጥቶበት ይዞታው እና በይዞታው ላይ የነበረው ቤት ሙሉ በሙሉ ከጥቅም ውጪ ስለሆነ ከቀድሞው ይዞታ 50 ሜትር ርቀት ላይ የሚገኘው በተጠሪ ስም የተመዘገበው ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት በተጠሪ እና በአካባቢው ሰው እገዛ ለሚች ወ/ሮ አየለች ኃይሌ ተሰርቶ በስማቸው የይዞታ ማረጋገጫ አውጥተው ለ7(ሰባት) ዓመት ከኖሩበት በኋላ በኑዛዜ ለተጠሪ እና ለልጃቸው ልጅ ስላስተላለፉ ተጠሪ ኑዛዜውን አፀድቀው ውርስ ከተጣራ በኋላ በስማቸው መመዝገቡን በማጣራት የተሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም፡፡ ተናዛዡ ፲ አለቃ ገ/.ማሪያም ዘለለው በወቅቱ የነበራቸው ሀብት በእጃቸው የነበረውን መኖሪያ ቤት መሆኑን በማያሻማ ሁኔታ ስለገለጹ አመልካች ኑዛዜውን አስመልክቶ ያቀረቡት መከራከሪያ ተቀባይነት የለውም፡፡ አመልካች የውርስ ጥያቄ ያነሱት ሟች አባታቸው ከሞቱ 9 ዓመት ከ5 ወር በኋላ ፣ እንዲሁም ሟች እያታቸው ከሞቱ 18 አመት እና 11 ወር ስላላፈው የአመልካች ክስ በይርጋ የታገደ ነው ሲል የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ብይን የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች የጠየቁት የሟች አባታቸው ውርስ 10 ዓመት አልሞላውም ማለቱ ሊታረም የሚገባ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካችም የሰበር አቤቱታውቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለ መልኩ የተመለከተው የግራ ቀኝ ክርክር እና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ውሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንፃር የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለው ሕግ እና የሰበር ሰሚ ችሎቱ በጉዳዩ ላይ ከሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ፍትህ የማግኘት መብት (Right to Access to Justice) በራሱ ሰብዓዊ መብት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ሌሎች ሰብዓዊ መብቶችን በተሟላ መልኩ ለማስከበር የሚያስችል መሰረታዊ መብት ነው፡፡ ይህ መብት ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸውና ባጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ሕግጋት፣ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶችና ዓለም አቀፍ ሠነዶች መርሆዎች ላይ እውቅና ያገኘ መብት ነው፡፡ በዓለም አቀፍ የሲቪልና ፖሊቲካ መብቶች ቃልኪዳን (International Covenant on Civil and Political Rights/ICCPR) አንቀጽ 2(3/ሀ እና ለ) ፣ አንቀጽ 26 ላይ ማንኛውም ሰው ፍትሕ የማግኘት

መብት እና በሕግ ፊት እኩል ሆኖ የመታየትና እኩል የሕግ ጥበቃ የማግኘት መብት እንዳለው ደንግጓል፡፡ በተባበሩት መንግስታት የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ (Universal Declaration of Human Rights) አንቀጽ 7፣8፣ እና 10 ላይ እንደተመለከተው ማንኛውም ሰው በየአገራቱ ሕግ ወይም ሕገ መንግስት በተደነገገው አግባብ ነጻና ገለልተኛ በሆነ አካል ፊት ቀርቦ መብቱን ማስከበር የሚያስችል ዳኝነታዊ መፍትሄ የማግኘት እና በሕግ ፊት እኩል ጥበቃ የማግኘት መብት እንዳለው ተደንግጓል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 37/1 ሥር ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ(ፍትህ) የማግኘት መብት እንዳለው ተደንግጓል፡፡ ፍርድ ቤቶች ይህን መብት የማክበርና የማስከበር ኃላፍነትና ግዴታ እንዳላባቸው ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 13/1 ድንጋጌ መረዳት ይቻላል። ፍትሕ የማግኘት መሠረታዊ መብት ዕውን ሊሆን የሚችለው የዳኝነት አካሉ ነፃና ገለልተኛ ሆኖ ፍትሐዊ በሆነ ሁኔታ የተከራካሪዎቹን ክርክር የመስማትና የሙግት ሂደቱን የመምራት ኃላፊነቱን የተወጣ እንደሆነው፡፡ ይህም ክርክሩ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ መቋጫ እስከሚያገኝበት ድረስ የዳኝነት አካሄዱ ፍትሐዊ ዝቅተኛ መስፈርቶችን(minimum requirements of fair trial) በሚያረጋግጥ መንገድ የመምራትና የመወሰን ኃላፊነት አለበት፡፡ የዳኝነት አካሉ ተከራካሪዎች ጉዳያቸውን ለማዘጋጀት የሚያስፈልጋቸውን በቂ ጊዜ መስጠት፣ በጠበቃ የመታገዝ መብታቸውን ማክበር፣ተከራካሪዎቹ ሙግቱን በማይረዱት ቋንቋ በሆነ ጊዜ የአስተርጓሚ ዕርዳታ የማግኘት፣የግራ ቀኙ የጽሑፍና የቃል ክርክር እና ማስረጃቸውን እንዲያቀርቡ ማድረግና መስማት ፣ የተቃራኒ ወገን ክርክር እና ማስረጃ ድርሷቸው የማስተባባል መብታቸውን መጠበቅ ፣ማስረጃዎቹን በመመርመር እና በመመዘን በበቂ ምክንያት የተደገፈ የተብራራ ፍርድ መስጠት ግዴታ እና ኃላፊነት እንዳለበት የሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 13/1 ፣ 37/1፣ 79/1 እና 2 ፣ እንዲሁም የሰበር ሰሚ ችሎቱ በሰበር መዝገብ ቁጥር 52540 ከሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ መረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም ለሰበር ሰሚ ችሎቱ የቀረበው የመጨረሻ ውሳኔ የዘጎችን መሠረታዊ ፍትሕ የማግኘት መብት(substantive justice)እና የሥነ ሥርዓት ፍትሕ (procedural justice) የጣሰ መሆኑ ከተረጋገጠ ስህተቱ መተራም አለበት፡፡

ክርክርን በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሰረት መምራት እና መቆጣጠር የፍርድ ቤቱ ኃላፊነት ሲሆን ክርክር በተገቢው ሁኔታ ካልተመራ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ዓላማዎች የሆኑትን እንደ አንጻራዊ እውነትን የመፈለግ ፣ ሥነ-ሥርዓታዊ ፍትህ ፣ ክርክርን ውጤታማ ፣ ወጭና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ መምራት የመሳሰሉትን ማሳካት ስለማይቻል የተከራካሪዎችን መብት ይነካል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ዳኝነት መስጠት የሚገባው የይግባኝ አቤቱታው ሥርዓቱን ተከትሎ የቀረበን ሲሆን ነው፡፡ ይግባኝ የተባለበትን ፍርድ ወይም ውሳኔ የሰጠው ፍርድ ቤት ነገሩን የወሰነው ክርክሩ ውስጥ ሳይገባ በመጀመሪያ ደረጃ የቀረበለትን መቃወሚያ ብቻ መሠረት በማድረግ ሲሆንና ይህ ፍርድ ወይም ውሳኔ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተለወጠ እንደሆነ የሚታዩ ነጥቦችን በመለየት ክርክሩ እንደገና

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

ወደ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተመልሶ እንዲታይ ማዘዝ እንደሚችል የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 341/1 ያመለክታል፡፡ በእርግጥ የድንጋጌው ይዘት ሲታይ አስገዳጅነት የሌለው(ፈቃጅ) ቢሆንም በግራ ቀኙ ተከራካሪዎች የሚቀርቡ የፍሬ ነገር ክርክሮችንና ማስረጃን በአግባቡ ለመስማት እና የተከራካሪዎቹን የይግባኝ መብት ላለማጣበብ ሲባል ጉዳዩ ወደ ሥር ፍርድ ቤት መመለስ እንዳለበት የሰበር ሰሚ ችሎቱ በሰበር መዝገብ ቁጥር 43331(በቅጽ 9 እንደታተመው)፤እንዲሁም በሰበር መዝገብ ቁጥር 163136(በቅጽ 24 እንደታተመው) አስገዳጅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች የስድስት ወር ህፃን እያሉ ጥር 11 ቀን 1986 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት የሟች አባታቸው አቶ ሽመልስ ገ/ማሪያም ዘለለው ወራሽነት በማረጋገጥ ህዳር 7 ቀን 2013 ዓ.ም ባቀረቡት ክስ ሰኔ 29 ቀን 1977 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት ሟች አያታቸው ሃምሳ አለቃ ገ/ማርያም ዘለለው ከሟች ባለቤታቸው ወ/ሮ አየለች ኃይሌ ገመዳ ጋር ያፈሩት በድሬደዋ ከተማ ቀበሌ 02 ውስጥ የሚገኝ ቁጥሩ 6469 የሆነው ቤት እና ኪራዩ ግማሽ ድርሻቸው ፤ እንዲሁም ሟች አባታቸው አቶ ሽመልስ ገ/ማርያም ሟች አያታቸው ፶ አለቃ ገ/ማርያም ዘለለው ፈቅደውላቸው በአከራካሪው ይዞታ ላይ የሰሩት አንድ ክፍል ቤት እንድወስንላቸው ያቀረቡትን ክስ ፤ አመልካች በ3 ዓመት ውስጥ ወራሽነታቸውን ስላላረጋገጡና ንብረቱም ከተያዘ 15 ዓ.ም ስላለፈው ያቀረቡት ክስ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ተጠሪ ክሱን የተቃወሙ ሲሆን አስቀድሞ የነበረው የቤት ቁጥር 494 በ1977 ዓ.ም መንገድ ወጥቶበት ሙሉ በሙሉ ፈርሶ በተጠሪ እና ባለቤታቸው እንዲሁም በሌሎች ሰዎች እገዛ የተሰራላቸውን አዲሱን የቤት ቁጥር 6469 ሟች ወ/ሮ አየለች ኃይሌ ገመዳ እንደተናዘዙላቸው ፤ በአመልካች አባት የተሰራ ቤት አለመኖሩን ጠቅሰው በክሱ ላይ የተመለከተው ቤት ከሚኖሩበት ቤት ጋር አይገናኝም የሚል የፍሬ ነገር ክርክር አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣን የተመለከተው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች የሚጠይቁት ሟች አያታቸው ፶ አለቃ ገ/ማርያም ዘለለው ሰኔ 29 ቀን 1977 ዓ.ም ትተው ያለፉትን የውርስ ሀብት ሲሆን ጥር 11 ቀን 1986 ዓ.ም አባታቸው አቶ ሽመልስ ገ/ማሪም ሲሞቱ አመልካች የ6(ስድስት ወር) ሕፃን ስለነበሩ 18(አሥራ ስምንት) ዓመት ከሞላቸው ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ ያለው ጊዜ ሲቆጠር ዘጠኝ ዓመት ከሁለት ወር እንዲሁም ሃምሳ አለቃ ገ/ማርያም ዘለለው ከሞቱበት ከሰኔ 29 ቀን 1977 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ ከ35 ዓመት በኋላ ያቀረቡት ክስ በይርጋ ቀር ነው የሚል ብይን ሰጥቷል፡፡ አመልካች ባቀረቡት ይግባኝ ጉዳዩን የተመለከተው ይግባኝ ሰሚው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች የጠየቁት ውርስ የሟች አያታቸው ሃምሳ አለቃ ገ/ማርያም ዘለለውን ሳይሆን ጥር 11 ቀን 1986 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት የሟች አባታቸው አቶ ሽመልስ ገ/ማሪምን ውርስ በመሆኑና አመልካች አባታቸው ሲሞቱ የ6(ስድስት) ወር ሕፃን ስለነበሩ በመብታቸው መሥራት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ከቻሉበት አንስቶ ክስ እስካቀረቡበት ድረስ ያለው ጊዜ ሲቆጥር 10(አሥር) ዓመት ስለማይሞላ አመልካች ያቀረቡት ክስ በይርጋ ይታገዳል በማለት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ብይን መሻሩ አግባብ ቢሆንም ፣ በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 826/2 መሠረት ለአመልካች የሚተላለፍ የውርስ ሀብት መኖር/አለመኖሩን ፣ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የፍሬ ነገር ክርክሩን በተመለከተ የአመልካች እና የተጠሪን ክርክር እና ማስረጃ ሰምቶ የሰጠው ውሳኔ ሳይኖር የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ ሳይሰማ የሰነድ ማስረጃውንና ከድሬደዋ አስተዳደር ቀበሌ 03 የቀረበውን መግለጫ መሠረት አድርጎ አመልካች ከሟች አባታቸው ሊተላለፍላቸው የሚችል መብት(ሊወርሱ የሚችሉት ንብረት) ለመኖሩ ማስረጃ አልቀረበም በሚል በውጤት ደረጃ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ብይን ማጽናቱ የአመልካችን የመሰማት መብት ከመንፈጉም በላይ የግራ ቀኙን የፍሬ ነገር እና ማስረጃ ክርክር ከመመርመር እና ከማጣራት አንፃር የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመጨረሻ የሥልጣን እርከን በመሆኑ የግራ ቀኙን የይግባኝ መብት የሚያጣብብ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ቀጣዩ ተወስኗል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 81031 መጋቢት 23 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ብይን እና ውሳኔ ፣ እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 19493 ግንቦት 21 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ፣ውሳኔ እና ትዕዛዝ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ- ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 9/1(ለ) መሠረት **ተሻሽሏል**።
2. አመልካች ያቀረቡት ክስ በይርጋ አይታገድም በማለት የተሰጠው የውሳኔ ክፍል አልተነካም(ፀንቷል)፡፡
3. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በውሳኔ የዘጋውን የመዝገብ ቁጥር 81031 አንቀሳቅሶ ለአመልካች የሚተላለፍ የውርስ ሀብት መኖር/አለመኖሩን አጣርቶ ሕጋዊ ውሳኔ እንዲሰጥ በሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 9/2 መሠረት መዝገቡ ተመልሶለታል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ. 252291

ቀን ፡- ጥቅምት 06 ቀን 2017 ዓ/ም

ዳኞች- እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች፡- ሕፃን እድላዊት ዮሐንስ አያሌው - ሞግዚት ወ/ሮ ሰላማዊት ኃይሌ - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1.ወ/ሮ አልማዝ አያሌው - ቀረቡ

2.ወ/ሮ አበባ አያሌው - ቀረቡ

3.አቶ ካሳሁን አያሌው - ቀረቡ

4.ወ/ሮ ጥሩወርቅ አያሌው - ወኪል 1ኛ ተጠሪ ቀረቡ

5. አቶ ደረጀ አያሌው - ወኪል 1ኛ ተጠሪ ቀረቡ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍርድ**

ጉዳዩ የውርስ ማጣራት ሥርዓትን የሚመለከት ሲሆን የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌደራል የመጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት በተደረገ ክርክር አመልካችና ተጠሪዎች ከሻሾችና ውርስ አጣሪዎች የነበሩ ሲሆን

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

መዝገቡ ላይ በሥር ተከሳሽ አልነበረውም፡፡ ግራቀኙ በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት አቤቱታ ይዘት ወላጅ እናታችን ወ/ሮ ተዋበች ዋቆ መግራ ሰኔ 23 ቀን 2014 ሞተዋል፣ ግራቀኙ የሟች ወራሾች መሆናቸውን በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 65611 በቀን 02/05/2015 እና በመ/ቁ 65605 በቀን 05/05/2015 አረጋግጠው ውርስ ለማጣራት እንዲፈቀድላቸው ጠይቀዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም ያለኑዛዜ ወራሾች ውርስ አጣሪ መሆን እንደሚችሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 947 የተገለጸውን መነሻ በማድረግ የግራቀኙን ጥያቄ ተቀብሎ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 944 የተቀመጠውን ውርስ የማጣራት ዓላማ ታሳቢ በአደረገ መልኩ ውርስ ተጣርቶ በፍ/ብ/ሕ/ ቁጥር 960(2) በተገለጸው አግባብ የውርስ አጣሪ ሪፖርት እንዲያቀርቡ በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ጥር 23 ቀን 2015 የውርስ አጣሪ ሪፖርት ቀርቧል፣ፍርድ ቤቱም የቀረበውን የውርስ አጣሪ ሪፖርት መርምሮ ውርሱ በአግባቡ የተጣራና ሪፖርቱም ተገቢውን የያዘ እንዲሁም ከሕግና ሞራል ጋር የማይቃረን መሆኑን በማረጋገጥ አጽድቆታል፡፡ አመልካች ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ይግባኙን በመመርመር ቅሬታ የቀረበበት ውሳኔ የሚነቀፍ ሆኖ ስላልተገኘ ይግባኙን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

አመልካች ነሐሴ 11 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይህን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ሲሆን ይዘቱም፡- በውርስ አጣሪው የቀረበው ሪፖርት የሚቾች ንብረት በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለከተማ ወረዳ 12 የቤት ቁጥር 488 ካርታ ቁጥር 37638 የተመዘገበ ቤት የገለፀ ቢሆንም በይዞታው ላይ ሰፍረው ስለሚገኙ የመኖሪያ ቤት እና በንግድ ቤት ወርሀዊ ኪራይ የሚሰበሰብባቸውንና ተጠሪዎች በንግድ ቤት እና በመኖሪያ ስለሚገለገሉባቸው ቤቶች መጠንና የሚሰበሰበው ገቢ በውርስ አጣሪው ሪፖርት ያለተካተተና ያልተገለጸ በመሆኑ ውርሱ በህጉ መሰረት አልተጣራም፤ የተጠሪዎች የውርስ ድርሻ 18.15 % ፣የአመልካች ድርሻ ደግሞ 9.25% ይሆናል በማለት የአመልካችን ድርሻ ከተጠሪዎች ድርሻ በግማሽ በመቀነስ የውርስ አጣሪ የሕፃኗን መብትና ጥቅም በሚጎዳ መልኩ የቀረበውን ሪፖርት አግባብ ካለመሆኑም በላይ የስር ፍርድ ቤት አግባብነቱን ሳይመረምር እና አስተያየት ሳንሰጥበት ከነጉድለቱ ተቀብሎ ማፅደቁ ተገቢነት የሌለው ነው፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የሰበር ሰሚው ችሎትም የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ በሥር ፍርድ ቤት በቀረበው የውርስ ሪፖርት ላይ አመልካች ተተኪ ወራሽ ሆነው በውርሱ የተሳተፉ ሲሆን በውርስ ሪፖርቱ ላይ ድርሻ ሲለይ ከተጠሪዎች ያነሰ ድርሻ ሆኖ ተመልክቷል፤ የውርስ ሪፖርቱን ፍርድ ቤቱ ሲያጸድቅ በውርስ ሕጉ መሰረት ድርሻው ያነሰበትን ምክንያት ሳያጣራና ሳይመረምር ማጽደቁ ሕጉን የተከተለ መሆን አለመሆኑ፣ አመልካች ሕጻን ከመሆናቸው አኳያ በኢፌዴሪ ሕገ - መንግስት አንቀጽ 36/2/ የተጠበቀላቸውን መብት ፍርድ ቤት ተገቢውን ጥበቃ ያደረገ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ታዟል፡፡

ተጠሪዎች ሰኔ 14 ቀን 2016 ዓ.ም የሰጡት መልስ ይዘት፡- አመልካችዋ በመዝገብ ቁጥር 188166 ጥር 23 ቀን 2015 ዓ.ም በቀረበው የውርስ ሀብት አጣሪ ሪፖርት ላይ በመስማት ስለትክክለኛነቱ ከአሁኑ ተጠሪዎች ተርታ ስማቸውን እና ፊርማቸውን አኑረው አረጋግጠዋል እያለ የውርስ አጣሪ ሪፖርት አልተመረመረም በማለት ያቀረቡት ጥያቄ ተገቢነት የሌለው ነው፣ ከቤት ኪራይ ከሚገኘው ገቢ ሁሉ ወራሾች እኩል እኩል መካፈል ሲገባን ተጠሪዎች አመልካች ህፃን እንደመሆኗ መጠን የወንድማችን ልጅ ስለሆነች መንከባከብ ስለሚጠበቅብን ከድርሻ በላይ በባንክ እየተላከላት ስለመሆኑ በቂ ማስረጃ ያለን እና በቅንነት ህፃኗ ከፍተኛ ደረጃ ላይ እንድትደርስ የምንፈልግ በመሆኑ ድርሻዋን በህጉ መሰረት ብታገኝ አንቃወምም፣ በውርስ ህጉም ሁሉም ወራሾች እኩል ማግኘት እንደሚገባን የተደነገገ ስለሆነ በውርስ ሪፖርት ላይ የአመልካች ድርሻ 9.25 እና ተጠሪዎች ግን 18.15 መሆኑ ቀርቶ እኩል እንድካፈል ቢወሰን አንቃወምም የሚል ነው፡፡ አመልካች በሰጡት የመልስ መልስ ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን በዚህ ችሎት ከተያዘው ጭብጥ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ግራቀኙ በሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ የሟች እናታቸው ወ/ሮ ተዋበች ዋቆ የውርስ ሀብት ይጣራልን በሚል ሲሆን በሥር ፍርድ ቤቶች አመልካችና ተጠሪዎች ራሳቸው የውርስ አጣሪ በመሆን የውርስ ሀብቱ ሪፖርት ለፍርድ ቤቱ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የቀረበው የውርስ ሪፖርት ለሕግና ለሞራል ተቃራኒ ባለመሆኑ ተቀባይነት አለው በማለት አጽድቆታል፡፡ አመልካች ያቀረቡት ይግባኝም ተቀባይነት ባለማግኘቱ የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው፡፡

ክርክሩን በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሰረት መምራት እና መቆጣጠር የፍርድ ቤቱ ኃላፊነት ሲሆን በተገቢው ሁኔታ ካልተመራ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ዓላማዎች የሆኑትን እንደ አንጻራዊ እውነትን የመፈለግ፣ ሥነ-ሥርዓታዊ ፍትህ፣ ክርክርን ውጤታማ፣ ወጭና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ መምራት የመሳሰሉትን ማሳካት ስለማይቻል የተከራካሪዎችን መብት ይነካል፡፡ ውርስ ማጣራት ሂደት በፍ/ሕ/ቁ. 948 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሠረት ኑዛዜ መኖር አለመኖሩ፣ የውርሱን ሀብት፣ ዕዳ፣ ወራሾችና ድርሻቸውን መለየት ሥራ የሚከናወንበት ሂደት ነው፡፡ ውርሱ ተጣርቶ እና ተለይቶ ለወራሾች የሚከፋፈል ሀብት ካለ የውርስ ክፍፍል የሚፈጸም ይሆናል፤ በመሆኑም ውርስ ማጣራት በራሱ የመጨረሻ ሂደት ሳይሆን በውርስ ንብረት ጉዳይ የመጨረሻ ሂደት ለሆነው የውርስ ሀብት ክፍፍል መነሻ ሁኔታ የሚፈጥር ነው፡፡ በውርስ ንብረት ጉዳይ የመጨረሻ ክንውን የውርስ ንብረት ክፍፍል ይሆናል ማለት ነው፡፡

የውርስ ማጣራት ሂደት ከሌሎች መደበኛ የክስ ሂደቶች የተለየ እና ከፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ በተጨማሪ በውርስ ሕጉ የተመለከቱ ሂደቶችን በማለፍ የሚከናወን ነው፡፡ የክርክር አመራር ሥርዓቱ ልዩ ባሕሪውን ባገናዘበ መልኩ የግራቀኙ የመደመጥ መብት መከበሩን ባረጋገጠ አግባብ መፈጸም አለበት፡፡ የክስ እና መልስ አቤቱታው ውርስ እንዲጣራ ከመጠየቅ ባለፈ ዝርዝር ፍሬ ነገሮችንና ክርክሮች የሚቀርቡበት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ባለመሆኑ ውርስ አጣሪ ተሹሞ የውርስ ሪፖርት ከቀረበ በኋላ ግራቀኙ ተከራካሪዎች ለፍርድ ቤቱ በውርስ ሪፖርቱ የኑዛዜ መኖር አለመኖርና ሕጋዊነቱ፣ ወራሾችና ያላቸው መብት ሆነ የውርስ ንብረት ዝርዝር ላይ ያላቸውን ክርክር የሚያቀርቡት ውርስ ሪፖርቱ ደርሷቸው የጽሁፍ አስተያየት/ክርክር እንዲያቀርቡ እድል በሚያገኙበት ጊዜ ነው፡፡ ግራቀኙ ያቀረቡትን ክርክር እርስ በእርስ እንዲለዋወጡና እንዲያውቁት ከተደረገ በኋላ የመደመጥ መብታቸው በተሟላ መልኩ በሚከበርበት አግባብ ክርክራቸው ሆነ ማስረጃ በመስማት በተነሱ ክርክሮች ላይ እልባት መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የውርስ ሪፖርቱን በሚመረምርበት ጊዜ የውርስ ማጣራት ተግባር ያስፈለገበትን ዓላማ መሠረት በማድረግ የውርስ ሕጉ መርሕዎችና ድንጋጌዎች መከበራቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

በተያዘው ጉዳይ ጥር 23 ቀን 2015 ዓ/ም በወራሾች የተዘጋጀው የውርስ ሪፖርት ለፍርድ ቤቱ የቀረበ ሲሆን በውርስ ሪፖርቱ 2.2. ላይ አመልካችና ተጠሪዎች የሟች የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች መሆናቸው ተገልጿል፤ ከውርስ ሀብቱ የውርስ ድርሻ በሪፖርቱ 4.1. ላይ ሲመለከት ደግሞ ተጠሪዎች እያንዳንዳቸው 18.15% ድርሻ አመልካች ደግሞ 9.25% ድርሻ ብቻ ያላቸው መሆኑ ተመዝግቧል፡፡ ተመሳሳይ ደረጃ ያሉ ወራሾች በፍ/ሕ/ቁ. 857 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሠረት በኑዛዜ ክፍፍል ሥርዓት የተለያየ ድርሻ ካልተሰጣቸው በስተቀር በሕግ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች እኩል መብት አላቸው፡፡ የቀረበው የውርስ ሪፖርት ኑዛዜ ሳይኖር በወራሾች መካከል ያልተገባ የውርስ ድርሻ ክፍፍል መመልከቱን የሚያሳይ ሆኖ እያለ የሥር ፍርድ ቤት የውርስ ሪፖርቱ ለሕግ ተቃራኒ አይደለም በማለት ማሻሻያ ሳያደርግ ማጽደቁ የውርስ ሪፖርቱን ከውርስ ሕጉ ጋር ተጣጥሞ የቀረበ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነቱን አለመወጣቱን ያሳያል፡፡ አመልካች ሕጻን እንደመሆናቸው መጠን በኢፌዴሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 36 ሕጻናት እኩል መብት ያላቸው መሆኑን እና ፍርድ ቤቶች የሕጻናት ደሕንነት መብት በቀደምትነት በማስከበር ረገድ የተጣለባቸውን ኃላፊነት መሠረት ያላደረገና መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 303634 ግንቦት 17 ቀን 2015 ዓ/ም እና የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 188186 ጥር 25 ቀን 2015 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1)(ለ) መሰረት ተሻሽሏል፡

2. የውርስ ንብረት የሆነው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለከተማ ወረዳ 11 የቤት ቁጥር 488 በካርታ ቁጥር 37638 ላይ ሟች አውራሻቸው ወ/ሮ ተዋበች ዋቆ ካላቸው ድርሻ ላይ አመልካች እና ተጠሪዎች እኩል 1/6ኛ የውርስ ድርሻ አላቸው በማለት የውርስ ሪፖርቱን በማሻሻል ወስነናል፡፡

3. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

<u>ማስታወሻ</u>፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ትዕዛዝ

- ❖ የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- ❖ በዚህ ችሎት የካቲት 06፣ የካቲት 13 እና የካቲት 20 ቀን 2016 ዓ/ም የተሰጠው እግድ ተነስቷል፤ይጻፍ
- ❖ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

መ/ዐ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ.መ.ቁ 252361

ቀን 27/02/2017 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** እትመት አሠፋ

ደረጀ አያና

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

ብርሃኑ መንግስቱ

አመልካች፡- ጉምሩክ ኮሚሽን ባህርዳር ቅ/ጽ/ቤት አልቀረቡም

ተጠሪ፡- አቶ ሀይለማርያም መለስ አልቀረቡም

መዝገቡ ለፍርድ የተቀጠረ ነው፡፡ በዚሁ አግባብ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካች በቀን 15/12/2015 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 261021 ግንቦት 29 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 229882 ግንቦት 30 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

ጉዳዩ ያልተከፈለን የቀረጥና ታክስ ክፍያ መሠረት በማድረግ ወለድ ሊከፈል አይገባም በማለት የቀረበን ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው ከፌዴራል ታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ ለአመልካች መስሪያ ቤት ባቀረቡት አቤቱታ አመልካች መስሪያ ቤት የአሲኩዳ ሲስተም ኤክሳይዝ ታክስ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የማይከፈልባቸው ዕቃዎች ላይ ከጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ መነሻ ወደ ተጨማሪ እሴት ታክስ ሲሸጋገር 1 በመቶ ሲቀንስ የነበረ በመሆኑ በሲስተም ችግር ምክንያት የተዘለለውን ቀሪ ቀረጥ እና ታክስ ተጠሪ እንዲከፍል ጠይቋል፤ ተጠሪ ቀረጥ እና ታክሱ እንዳይከፈል ያደረግኩት ነገር የለም፤ አመልካች ቀረጥ እና ታክሱን ማስከፈል ይችላል ቢባል እንኳን ወለድ መታሰቡ ከጉምሩክ አዋጅ ውጪ ስለሆነ ውሳኔው ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ አመልካችም የተጠሪን አቤቱታ ከመረመረ በኋላ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 122 በማናቸውም ምክንያት ያልተከፈለ ወይም ሊከፈል ከሚገባው ያነሰ መሆኑ በድሕረዕቃ አወጣጥ ኦዲት የተደረሰበት እንደሆነ ባለሥልጣኑ ዲክላራሲዮን አቅራቢውን ያልተከፈለውን ወይም በልዩነት ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ ሳይከፈል ከቀረበት ቀን ጀምሮ በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሊያስከፍል ይችላል በማለት የተደነገገ በመሆኑ ተጠሪ እንዲከፍሉ የተጠየቀው ቀረጥ እና ታክስ እንዲሁም ወለድ ተገቢ ነው ሲል የተጠሪን አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል፡፡

ተጠሪ ይህን ውሳኔ በመቃወም ለታክስ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት የታክስ ይግባኝ ጉባኤም ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ ተጠሪ እንዲከፍሉ የተጠየቀው ቀረጥና ታክስ ከጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 122 አንጻር ሲታይ ተገቢ ነው፤ ወለድን በተመለከተም ወለድ የገንዘብ ዋጋ በመሆኑ ሊከፈል የሚገባው ቀረጥና ታክስ ባለመከፈሉ እና ገንዘቡም በወቅቱ ለአመልካች ገቢ ያልተደረገ በመሆኑ ወለድ እንዲከፈል መደረጉ ተገቢ ነው ሲል የተጠሪን መስሪያ ቤት ውሳኔ አጽንቶታል፡፡

ተጠሪ በመቀጠል ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 122(1) ቀረጥና ታክሱ ያልተከፈለ ወይም ሊከፈል ከሚገባው ያነሰ መሆኑ በድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት የተደረሰበት እንደሆነ ባለስልጣኑ ዲክላራሲዮን አቅራቢውን ያልተከፈለውን ወይም በልዩነት ሊከፍል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ ሳይከፍል ከቀረበት ቀን ጀምሮ በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሊያስከፍል እንደሚገባ ተደንግጎ ይገኛል፤ ተጠሪ ያልተከፈል ቀሪ ቀረጥ እና ታክስ እንዳለ ያልካዱ በመሆኑ በዚህ ረገድ በባለስልጣኑ መስሪያ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው፤ ለቀረጥ እና ታክሱ ያለመከፈል ምክንያት የሆነው ዲክላራሲዮን አቅራቢው ተጠሪ ሳይሆን አመልካች ለመሆኑ ተረጋግጧል፤ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 122(2) ላይ ለቀረጥ እና ታክስ ያለመክፈል ወይም በመነሻ መክፈል ምክንያት የሆነው ዲክላራሲዮን አቅራቢው የሆነ እንደሆነ ሳይከፈል በቀረው ቀረጥ እና ታክስ ለይ አስር በመቶ ቅጣትና የባንክ ወለድ ተጨምሮ እንደሚከፍል ተመልክቷል፤ ይህ ድንጋጌ የአንቀጽ 122(1) ቀጣይ ሲሆን በድንጋጌው ግልባጭ ንባብ መሰረት ለቀረጥ እና ታክሱ ያለመክፈል ምክንያት የሆነው ዲክላራሲዮን አቅራቢው ካልሆነ ሳይከፈል በቀረው ቀረጥ እና ታክስ ላይ ቅጣትም ሆነ ወለድ የመክፍል ሀላፊነት የለበትም፤ ተጠሪ ያልተከፈለውን ቀሪ ቀረጥ እና ታክስ ከመክፈል ውጪ ወለዱን የመክፈል ሀላፊነት የለባቸውም በማለት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የታክስ ይግባኝ ኮሚሽኑ የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል ተጠሪ ያልተከፈለውን ቀሪ ቀረጥ እና ታክስ እንዲከፍሉ መወሰኑ በአግባቡ ሲሆን ወለድ ግን የመክፍል ሀላፊነት የለባቸውም ሲል ወስኗል፡፡

አመልካች በበኩሉ ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም ውሳኔው ሳይለወጥ ቀርቷል፡፡

አመልካች ነሐሴ 15 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፎ ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ይህን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ሲሆን ይዘቱም፡- በተጠሪ መከፈል የነበረበት ቀሪ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈል የቀረ ስለመሆኑ አመልካች ባከናወነው ኦዲት ተረጋግጧል፤ ይሁን እንጂ ቀረጥ እና ታክሱ በማነስ የተከፈለው በጊዜው በነበረው የሲስተም ችግር ምክንያት በመሆኑ አመልካች በተጠሪ ላይ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 122(2) መሰረት ከቅጣት ክፍያ ነጻ አድርጎታል፤ ሆኖም ይህ ድንጋጌ ተጠሪን ያልተከፈለውን ቀረጥ እና ታክስ እንዲሁም የዚህን ገንዘብ ወለድ ከመክፈል ነጻ አያደርጋቸውም፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በዚህ ረገድ በሰ.መ.ቁ 219003 አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፤ ስለሆነም ይህ ታልፎ በስር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ተጠሪ ሊከፍሉት ሲገባ ያልከፈሉት ተጨማሪ ቀረጥ እና ታክስ ስለመኖሩ ባላከራከረበት ሁኔታ ቀሪ ቀረጥና ታክሱ ያልተከፈለው በተጠሪ ጥፋት ባለመሆኑ ባልተከፈለው ክፍያ ላይ ተጠሪ ወለድ ሊከፍሉ አይገባም በማለት የመወሰኑን አግባብነት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 219003 ከሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ጋር በማገናዘብ ሊመረመር የሚገባው ሆኖ በመገኘቱ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2/4(ሸ) መሠረት ተጠሪ እንዲቀርቡ ታዟል፡፡

ተጠሪ በአዲስዘመን ጋዜጣ ጥሪ ተላልፎላቸው ስላልቀረቡ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ የቻልነው አመልካች መስሪያ ቤት ባደረገው የድሕረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት የአሲኩዳ ሲስተም ኤክሳይዝ ታክስ የማይከፈልባቸው ዕቃዎች ላይ ከጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ መነሻ ወደ ተጨማሪ እሴት ታክስ ሲሸጋገር 1 በመቶ ሲቀንስ የነበረ በመሆኑ በሲስተም ችግር ምክንያት የተዘለለ እና ተጠሪ ያልከፈሉት ቀሪ ቀረጥ እና ታክስ እንዳለባቸው፤ ተጠሪ ለቀረጥ እና ታክሱ አለመከፈል ምክንያት አለመሆናቸው፤ አመልካቹም ይህንኑ ተከትሎ ተጠሪ ያልተከፈለውን ቀረጥና ታክስ ከነወለዱ እንዲከፍሉ የጠየቀ መሆኑን እና ቅጣቱን እና ያላካተተ መሆኑን ነው፡፡ ስለሆነም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚፈልገው

የክርክሩ መሠረታዊ ጭብጥ ዲክላራሲዮን አቅራቢው ለቀረጥ እና ታክሱ ያለመከፈል ምክንያት ካልሆነ ሳይከፈል ለቀረው ቀረጥ እና ታክስ ቅጣት እንዳይከፍል ከማድረግ ባለፈ ወለድ የመክፈል ሀላፊነቱን ያስቀርበታል? ወይስ አያስቀርበትም? የሚለው ነው፡፡

የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 122(1)(2) ድንጋጌ ቀረጥና ታክስ በማናቸውም ምክንያት ያልተከፈለ ወይም ሊከፈል ከሚገባው ያነሰ መሆኑ በድሕረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት የተደረሰበት እንደሆነ ባለስልጣኑ ዲክላራሲዮን አቅራቢውን ያልተከፈለውን ወይም በልዩነት ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥ እና ታክስ ሳይከፈል ከቀረበት ቀን ጀምሮ በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሊያስከፍል ይችላል ሆኖም ድንጋጌ ለቀረጥ እና ታክሱ ያለመከፈል ወይም በማነስ መከፈል ምክንያት የሆነው ዲክላራሲዮን አቅራቢው የሆነ እንደሆነ ሳይከፈል በቀረው ቀረጥ እና ታክስ ላይ አሥር በመቶ ቅጣት እና የባንክ ወለድ ተጨምሮ ይከፈላል በማለት ይደነግጋል፡፡ የዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) ባለስልጣኑ ኦዲት የሚያደርግ መሆኑን በጽሑፍ ካሳወቀ በኋላ ዲክላራሲዮን አቅራቢው ያልተከፈለ ቀረጥ እና ታክስ መኖሩን ከገለጸ እና ለመክፈል ፈቃደኛ ከሆነ ከቀረጥ እና ታክሱ እና ወለዱ ክፍያ በስተቀር ቅጣት እንዳይጣልበት ባለስልጣኑ ሊወስን ይችላል በማለት ይደነግጋል፡፡ ከድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መገንዘብ እንደሚቻለው በድሕረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት የተደረሰበት ሊከፈል የሚገባው ወይም ሳይከፈል የቀረ ቀረጥ እና ታክስ መኖሩ ከተረጋገጠ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ቀረጥና ታክሱ ሳይከፈል ከቀረበት ቀን ጀምሮ በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ማስከፈል እንደሚችል፣ ዲክላራሲዮን አቅራቢው ለቀረጥ እና ታክሱ ያለመከፈል ወይም በማነስ መከፈል ምክንያት ካልሆነ ሳይከፈል ከቀረው ቀረጥ እና ታክስ እና ወለዱ ክፍያ በስተቀር ቅጣት እንዳይጣልበት ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ሊወስን እንደሚችል ነው፡፡

በኢትዮጲያ በ 2016 ዓ.ም የታተመው ዐውደ ጥበባዊ የሕግ መዝገበ ቃላት ወለድ በብድር ለተወሰደ ወይም በባንክ ለተቀመጠ ገንዘብ ወይም <u>በወቅቱ ላልተከፈለ ዕዳ የሚፈጸም ተጨማሪ ክፍያ ነው፣</u> የወለድ ጽንስ ሐሳብ ዓላማ አንድ ባለገንዘብ ገንዘቡን ለሌላ ሰው በመስጠቱ ምክንያት ለደረሰበት የአደጋ ተጋላጭነት ወይም <u>ገንዘቡን ራሱ ለመጠቀም ያለውን ዕድል መስዋዕት በማድረጉ ምክንያት ገንዘቡን የተጠቀመበት ሰው ላገኘው ጥቅም ካሳ እንዲከፍለው ማድረግን ታሳቢ ያደረገ፣</u> በብድር በተገኘ ወይም እንዲቀመጥ በተሰጠ ገንዘብ በመጠቀም ለተገኘ ጥቅም ለባለገንዘቡ በመደበኛነት በተወሰነ ተመን የሚከፈል ገንዘብ፣ <u>መከፈል በሚገባው ጊዜ ላልተከፈለ ገንዘብ በሕግ የተፈቀደ ወይም በተዋዋይ ወገኖች የተወሰነ፣</u> በዋናው ገንዘብ ላይ በመቶኛ የሚሰላ መካሻ ወይም ጥቅም ነው በሚል ተተርጉሟል፡፡ / ሰረዝ የተጨመረበት /

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 219003 በሰጠው ውሳኔ ወለድ በወቅቱ ሊከፈል ይገባው የነበረ ዋናው ገንዘብ ባለመከፈሉ ክፍያው ለዘገየበት የሚከፈል ክፍያ በመሆኑ በወቅቱ ባልተከፈለ ገንዘብ ላይ በባለመብቱ የሚጠየቅ የወለድ ጥያቄ ሊከፈል የሚገበው መሆኑን በመግለጽ በየትኛውም እርከን ላይ ለሚገኙ ፍርድ ቤቶች አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በያዝነው ጉዳይ የአሁን ተጠሪ ለቀረጥ እና ታክሱ አለመከፈል ምክንያት ባለመሆናቸው ከቅጣት ነጻ ተደርገዋል፡፡ ሆኖም አመልካች በራሱ ችግር ምክንያት ቢሆንም በወቅቱ ሊከፈል ይገባው የነበረ ገንዘብ ያልተከፈለው እና ገንዘቡ በተጠሪ እጅ የቆየ በመሆኑ ተጠሪ በወቅቱ ለአመልካች ባልተከፈለው እና በእጃቸው ለቆየው ገንዘብ ለአመልካች ሕጋዊ ወለድ የመክፈል ግዴታ አለባቸው፡፡ ስለሆነም ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን በዚህ አግባብ በማየት መወሰን ሲገባቸው ተጠሪ ለቀረጥ እና ታክሱ አለመከፈል ምክንያት ስላልሆኑ ወለድ የመክፈል ግዴታ የለባቸውም በማለት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 261021 ግንቦት 29 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 229882 ግንቦት 30 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1(ለ) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል ታክስ ይግባኝ ኮሚሽን በመ.ቁ B-373 ሕዳር 03 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ጸንቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
   - መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ/ጋ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የመ.ቁ.252442

ጥቅምት 08/2017 ዓ.ም

ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

ሀብታሙ እርቅይሁን

**አመልካች፡** ወ/ሮ ሳምራዊት ምንዳ አልቀረቡም

**ተጠሪ፡** አቶ አበባው መንግስት ጠ.አቶ ውብሸት ይመኑ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

በመዝገቡ ላይ የቀረበው ጉዳይ የባልና ሚስት ንብረት ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/303781 ላይ ሰኔ 06/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የአመልካችን የይግባኝ አቤቱታ ውድቅ ያደረገበትን ብይን በመቃወም ነው፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበውም በግራ ቀኙ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍርድ ቤት ውሳኔ ቀሪ የተደረገው ሰኔ 30/2014 ዓ.ም ሆኖ እያለ ግራ ቀኙ ተለያየተው መኖር ከጀመሩበት ሰኔ 25/2013 ዓ.ም ጀምሮ በአሁን ተጠሪ ስም በባንክ የተቆጠበው ገንዘብ የጋራ ባለመሆኑ አመልካች ሊካፈሉት አይገባም በሚል

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የመወሰኑን አግባብነት ይኸው ችሎት በመ/ቁ/242811 ላይ ከሰጠው ትርጉም አኳያ መርምሮ ለመወሰን ነው፡፡

ክርክሩ የጀመረው በግራ ቀኙ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍቺ መጠናቀቁን ተከትሎ የአሁን አመልካች በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት የጋራ ንብረት ክፍፍል ጥያቄ ነው፡፡ በክርክሩም ወ/ሮ አዲሴ መንግስት የተባሉት የአሁን ተጠሪ እህት በጣልቃ ገብነት ቀርበው ተከራክረዋል፡፡ አመልካች የክፍፍል ጥያቄ ካቀረቡባቸው ንብረቶች ውስጥ ለዚህ ሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ግራ ቀኙ ከተለያዩበት ሰኔ 25/2013 ዓ.ም ጀምሮ የፍቺ ውሳኔ እስከተሰጠበት ሰኔ 30/2014 ዓ.ም ድረስ በተጠሪ ስም በአቢሲንያ ባንክ እና በኢትዮጲያ ንግድ ባንክ የተቆጠበው ገንዘብ ወይም ወጪ የተደረገው ገንዘብ ተጣርቶ እንዲወሰን የቀረበው የዳኝነት ጥያቄ ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ ለዚሁ የአመልካች የክፍፍል ጥያቄ በሰጡት መልስ በስሜ በባንክ የተጠራቀመ ገንዘብ እንደሌለ፤ ቢኖር እንኳን ገንዘቡ የተፈራው አመልካች እና ተጠሪ ተለያይተው አመልካችዋ ኑሮዋቸውን በአሜሪካን ሀገር አድርገው ይኖሩ በነበረበት ወቅት በመሆኑ በተጠሪ የግል ጥረት የተፈራ እንጂ የጋራ ንብረት ባለመሆኑ አመልካች ሊካፈሉ አይገባም፤ ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ወቅት የወጣ ወጪም ለትዳር ጥቅም እንደወጣ ግምት የሚወሰድበት በመሆኑ የክፍፍል ጥያቄ ሊቀርብበት የሚገባ ባለመሆኑ ከዚህ አኳያ የቀረበው ጥያቄ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ በሰጠው ውሳኔ ግራ ቀኙ ከሰኔ 25/2013 ዓ.ም ጀምሮ ተለያይተው ይኖሩ የነበረ ስለመሆኑ ያላከራከረ ሲሆን ከዚህ ጊዜ በኋላ አመልካች በባንክ ሂሳቡ ላይ ገንዘብ ገቢ ስለማድረጋቸው እና ለገንዘቡ መፈራት አስተዋጽኦ የነበራቸው ስለመሆኑ ያላስረዱ በመሆኑ ሊካፈሉት የሚገባ አይደል በሚል ምክንያት ውድቅ አድርጎ ከሰኔ 25/2013 ዓ.ም በፊት የተቆጠበውን ገንዝብ ብቻ አጣርቶ እንዲካፈሉ ወስኗል፡፡ አመልካች ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ በኤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም ፍርድ ቤት አቤቱታውን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 337 መሰረት ሰርዟል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ላይ ነው፡፡ አመልካች ነሐሴ 17/2015 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እና ትዕዛዝ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ ከላይ በዚህ ፍርድ መግቢያ ላይ የተጠቀሰውን ነጥብ አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል ተብሎ በዚሁ ነጥብ ላይ ግራ ቀኙ የበኩላቸውን የጽሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና መሰረታዊ የክርክሩ ይዘት ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ከሆነው የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ አመጣጥ መገንዘብ እንደሚቻለው ግራ ቀኙ ከሰኔ 25/2013 ዓ.ም ጀምሮ ተለያይተው መኖር የጀመሩ ቢሆንም በመካከላቸው የነበረው ጋብቻ በፍርድ ቤት ውሳኔ ቀሪ የተደረገው ሰኔ 30/2014 ዓ.ም ነው፡፡ እንግዲህ በጋብቻ ፍቺ እና በፍቺ ውጤት ላይ የመወሰን ሥልጣኑ የፍርድ ቤት ብቻ በመሆኑ ግራ ቀኙ ለአንድ አመት አካባቢ ተለያይተው መኖር የጀመሩ ቢሆንም ጋብቻቸውን አስምልክቶ በፍርድ ቤት የፍቺ ውሳኔ እስከተሰጠበት ቀን ድረስ ጋብቻው ህልዎት የነበረው ነው፡፡ በህግ አግባብ የተመሰረተ ጋብቻ ደግሞ ከሚያስከትላቸው ውጤቶች ውስጥ አንዱ በተጋቢዎቹ መካከል የጋራ የንብረት ባለቤትነትን (Communality of Property/ የሚያቋቁም መሆኑ ነው፡፡ በዚሁ አግባብ ተጋቢዎች ጋብቻቸውን ከፈፀሙበት ቀን ጀምሮ በጋብቻ ውስጥ የሚያፈሯቸው ንብረቶች በሙሉ የጋራ ንብረት ናቸው ተብሎ የህግ ግምት እንደሚወሰድ በተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 57 እና 62 ስር ተመልክቷል፡፡ በእነዚህ ህግጋት ንብረትን አስመልክቶ የተወሰደው ህጋዊ ግምት ተጋቢዎች የአስተዋጽዋቸው ደረጃ የተለያየ ቢሆንም በጋብቻ ውስጥ በሚፈራው ንብረት መገኘት ላይ የየራሳቸው የዓይነትም ሆነ የአገልግሎት አበርክቶ ይኖራቸዋል በሚል መነሻነት ነው፡፡

እርግጥ ነው የጋብቻ መኖር እና የጋብቻ ውጤት መኖር የተለያዩ በመሆኑ ሁለቱን ጉዳዩች ነጣጥሎ ማየት እና በዚያው ልክ መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ጋብቻ ተቋም በመሆኑ የሚቋቋመውም ሆነ ቀሪ የሚሆነው በህግ በግልፅ ተለይቶ በተመለከተው አኳኋን ብቻ በመሆኑ የጋብቻ መኖር አለመኖር ጉዳይ የህግ ጉዳይ ነው፡፡ በአንፃሩ ጋብቻው የሚያስከትለው ውጤት ተጋቢዎቹ በመጋባታቸው ምክንያት የተፈጠረ እና በህግ ግምት የሚወሰድበት የሁኔታ ለውጥ በመሆኑ የውጤቱ መኖር ያለመኖር የፍሬ ነገር ጉዳይ ይሆናል፡፡ ጋብቻ ከሚያስከትላቸው ውጤቶች ውስጥም ተለያይቶ ለመኖር በተጋቢዎቹ መካከል የተደረገ ስምምነት ከሌለ በቀር አብሮ መኖር፤ ቤተሰብን በጋራ መምራት/ማስተዳደር፤ መተጋገዝ እና መደጋገፍ፤ መኖሪያ ስፍራንም ሆነ የጋራ ንብረትን አስምልክቶ የጋራ ውሳኔ መስጠት፤ እንደአቅማቸው እና ገቢያቸው መጠን ለትዳር ወጪያቸው አስተዋፅዖ ማድረግ እና የመሳሰሉት መሆኑን ከተሻሻለው የፌዴራል መንግስት የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 49፣ 50፣ 53-55፣ እና 72 ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡

ከህግ አኳያ የጋብቻ መኖር የጋብቻው ውጤት የሆነው የጋራ ንብረት ባለቤትነት መብት ስለመኖሩ በህግ ረገድ የተቀመጠውን ግምት ከሚያስወስድ በቀር በራሱ ስለውጤቱ መኖር ብቸኛ መረጋገጫ ባለመሆኑ ጋብቻው በንብረት ረገድ የሚያስከትለውን ውጤት ከጋብቻው መኖር ነጥሎ ማየት ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም ቀድሞ የተፈፀመው ጋብቻ ህጋዊ ስርዓቱን ጠብቆ በፍርድ ቤት ውሳኔ ቀሪ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ባለመደረጉ ጋብቻው አለ የሚባል ቢሆንም ተጋቢዎቹ ከስምምነት ውጭ በገዛ ፈቃዳቸው ለረጅም ጊዜ ተለያይተው የየራሳቸውን ህይወት በመኖራቸው ምክንያት የጋብቻው ውጤት በተጨባጭ ያልነበረ መሆኑን ማረጋገጥ ከተቻለ የጋብቻው ውጤት ነው ተብሎ በንብረት ረገድ የተወሰደውን የህግ ግምት ቀሪ ማድረግ ይቻላል፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ ግራ ቀኙ ተለያይተው የኖሩት ጋብቻቸው በፍርድ ቤት ውሳኔ ቀሪ ከመደረጉ በፊት ለአንድ ዓመት አካባቢ ብቻ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥም ቢሆን የግራ ቀኙ ተለያይቶ መኖር የየራሳቸውን ህይዎት ለመምራት መሆኑን፤ በዚሁ ሂደትም አንደኛው ተጋቢ ያለሌላኛው ተጋቢ የገንዘብ፤ የዓይነት፤ የአገልግሎት ወይም ሌላ ማናቸውም አበርክቶ ሀብት/ንብረት ያፈራ ስለመሆኑ እና በጥቅሉ የጋብቻ ውጤቱ በተጨባጭ ያልነበረ ለመሆኑ የተረጋገጠ ነገር ባለመኖሩ በተጋቢዎቹ የተፈራው ንብረት የጋራ ንብረት በሚለው የህግ ግምት ውስጥ የሚጠቃለል ነው፡፡

ከዚህ አኳያ የስር ፍርድ ቤቶች ግራ ቀኙ ለአንድ ዓመት ተለያይተው በመኖራቸው ብቻ አመልካች በዚህ ጊዜ ውስጥ በተጠሪ ስም በባንክ የተቀመጠን ገንዘብ ሊካፈሉ አይገባም በሚል መወሰናቸው የጋብቻ ውጤትን አድማስ ያላገናዘበ እና የቤተሰብ ህጉንም መሰረታዊ ዓላማ እና መንፈስ ያልተከተለ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ**

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/103092 ላይ የካቲት 30/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት ግራ ቀኙ ተለያይተው መኖር ከጀመሩበት ሰኔ 25/2013 ዓ.ም በኋላ በተጠሪ ስም በባንክ አለ የተባለውን ገንዘብ አመልካች ሊካፈሉ አይገባም በሚል የሰጠው የውሳኔ ክፍል፤ ይህንኑ በማፅናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/303781 ላይ ሰኔ 06/2015 ዓ.ም የሰጠው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥት 348/1/ እና የፌዴራል የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9/1/ለ// መሰረት ተሽረዋል፡፡ ሌላው የውሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡

2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በውሳኔ የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳስ ግራ ቀኙ ተለያይተው መኖር ከጀመሩበት ሰኔ 25/2013 ዓ.ም ጀምሮ የፍቺ ውሳኔ እስከተሰጠበት ሰኔ 30/2014 ዓ.ም ድረስ በተጠሪ ስም በባንክ የተጠራቀመ ገንዘብ መኖር አለመኖሩን፤ የተቆጠበ ገንዘብ ካለ በዚሁ ጊዜ ውስጥ ለትዳር ጥቅም የወጣ እና መጠኑም ምን ያክል እንደሆነ በተገቢው መንገድ ካጣራ በኋላ በውጤቱ ላይ የመሰለውን እንዲወስን ጉዳዩን መልሰንለታል፡፡

**<u>ትዕዛዝ</u>**

1. የዚህን ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

2. በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ ካለ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ/ጋ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የሰ/መ/ቁ 252645

ጥቅምት 27 ቀን 2017 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ብርቅነሽ እሱባለው

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች ፡- አቶ ኡስማን ሰዒድ

ተጠሪ፡- በኢፌዴሪ ጉምሩክ ኮሚሽን አዋሽ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ነ/ፈጅ ቴዎድሮስ ሀይሌ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የጉምሩክ ሠራተኛ የሥራ ክርክርን በተመለከተ ተፈጻሚነት ያለው ሕግ የትኛው ነው የሚለውን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው በሥር ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ሲሆኑ ተጠሪ ተከሳሽ ነበር፡፡ አመልካች በተጠሪ መሥሪያ ቤት ሠራተኛ ሆነው ሲያገለግሉ የነበሩ ሲሆን የተጠሪ አዋሽ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሕዳር 09 ቀን 2014 ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ አመልካች ከመስከረም 08 ቀን 2014 ዓ/ም ጀምሮ ከሥራ ቦታቸው ያልተገኙ በመሆኑ በፌዴራል መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 አንቀጽ 86(4) መሠረት ከሥራ አሰናብቷል፡፡ አመልካች ታህሳስ 23 ቀን 2014 ዓ/ም ለተጠሪ ዋና መሥሪያ ቤት ቅሬታ ያቀረቡ ሲሆን ጥር 25 ቀን 2014 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ አመልካች በደንብ ቁጥር 155/2000 አንቀጽ 42(1)

መሠረት ከሥራ ቦታቸው ከቀሩ በሦስት ወር ውስጥ ለመመለስ ያላመለከቱ በመሆኑ ወደሥራቸው ሊመለሱ አይገባም በማለት አስተዳደራዊ ውሳኔ ሰጥቷል።

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የካቲት 14 ቀን 2014 ዓ/ም በተጻፈ ይግባኝ ማመልከቻ ለፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም ከሥራ ፈቃድ ወስጄ ወደኮምቦልቻ ከተማ የሄድኩ ሲሆን በጊዜው ሕመምና ሀዘን አጋጥሞኝ ነበር፣ ከጥቅምት 04 ቀን 2014 ዓ/ም ጀምሮ ደግሞ በጊዜው በነበረው ጦርነት መድፍ ሲተኮስ ስለነበር የትራንስፖርት አገልግሎት ተቋርጧል፣ ጥቅምት 21 ቀን 2014 ዓ/ም ጀምሮ ደግሞ ኮምቦልቻ ከተማ በጦርነቱ የተያዘች በመሆኑ ወደሥራ ገበታዬ መመለስ አልቻልኩም። የፌዴራል መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 ሆነ በደንብ ቁጥር 155/2000 ባልተከተለ መንገድ የሥራ ውሌ መቋረጡ ሕገ-ወጥ በመሆኑ ያልተከፈለኝ ደመወዝ ተከፍሎኝ ወደሥራ እንድመለስ ይወሰንልኝ የሚል ነው።

ተጠሪ ባቀረበው መልስ በጉምሩክ ሠራኞች ደንብ ቁጥር 155/2000 አንቀጽ 42 መሠረት ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ከሥራው ያልተገኘ ሠራተኛ ወደሥራው ሊመለስ እንደሚችል ተመልክቷል፣ አመልካች በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ወደሥራ ለመመለስ አላመለከቱም፣ ከሦስት ወር በኋላ ግን ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ቢኖርም ወደሥራ መመለስ የማይቻል ስለመሆኑ ከአንቀጽ 42(1) ድንጋጌ የምንገነዘበው ነው፣ አመልካች በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ወደሥራ ለመመለስ ያላመለከቱ በመሆኑ ወደሥራ ገበታቸው ሊመለሱ አይገባም ተብሎ የተጠሪ መሥሪያ ቤት ውሳኔ እንዲጸና ጠይቋል።

የአስተዳደር ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 336/14 ላይ ግራቀኙን አከራክሮ አመልካች ወደሥራ ቦታቸው ያልተመለሱት በጊዜው በነበረ ጦርነት ምክንያት ሲሆን ይሕም ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት በመሆኑ ተጠሪ አመልካችን ከሥራ ማሰናበቱ ከርዕትም አንጻር ሲታይ አግባብ ባለመሆኑ ያልተከፈላቸው ደመወዝ ተከፍሎ ወደሥራ ቦታቸው እንዲመለሱ በማለት ወስኗል። ተጠሪ ያቀረበውን ይግባኝ ተቀብሎ ያከራከረው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በበኩሉ ለጉምሩክ ሠራተኛ ተፈጻሚነት ያለው ሕግ የፌዴራል የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 ሳይሆን ደንብ ቁጥር 155/2000 ስለመሆኑ በበሰር ችሎቱ በመዝብ ቁጥር 255811 ላይ ትርጉም ተሰጥቶበታል፣ አመልካች ከሥራ ቦታቸው ያልተገኙት በሕመም፣ በሀዘንና በጦርነት ምክንያት መሆኑ የተረጋገጠ ቢሆንም በደንብ ቁጥር 155/2000 አንቀጽ 42(1) መሠረት በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ወደሥራ ለመመለስ ያላመለከቱ በመሆኑ የሥራ አገልግሎታቸው ተቋርጧል፣ አመልካች ወደሥራ ቦታቸው ሊመለሱ አይገባም በማለት የአስተዳደር ፍርድ ቤቱን ውሳኔ በመሻር የተጠሪ መሥሪያ ቤት የሰጠውን የማሰናበት ውሳኔ አጽንቷል።

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው። አመልካች በ17/12/2015 ዓ/ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም በደንብ ቁጥር 155/2000 አንቀጽ 42 መሠረት አንድን ሠራተኛ በሦስት ወር ጊዜ በሥራ ቦታው አልተገኘም በማለት ለመወሰን በዚህ ጊዜ ውስጥ የሥራ ውሉ ጸንቶ መቆየት አለበት፣

አመልካች የሥራ ውሌ የተቋረጠ ሕዳር 09 ቀን 2014 ዓ/ም ሲሆን በዚህ ጊዜ ሦስት ወር አልሞላም፣ አመልካች ወደስራ ለመለስ ያመለከትኩበትን ታህሳስ 23 ቀን 2014 ዓ/ም ድረስ በመቁጠር በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ በሥራ ቦታህ አልተገኘህም መባሌ ተገቢ አይደለም፣ ከሥራ የቀረሁትም በበቂ ምክንያት ስለመሆኑ በሥር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፣ ስለሆነም ውሳኔው የሕግና የማስረጃ ምዘና ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተሽሮ ወደሥራዬ ልመለስ ይገባል የሚል ነው፡፡

የሰበር ችሎቱ ጉዳዩን ተመልክቶ አስተዳደር ፍርድ ቤቱ ከሰጠው የፍሬ ነገር ድምዳሜ፣ ተጠሪ ከአንድ ወር በላይ በሥራ ቦታህ አልተገኘህም በማለት ከጻፈው የስንብት ደብዳቤ አንጻር የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ወደስራህ አልተመለስክም በማለት መወሰኑ ሲታይ ማስረጃ መመዘን አለመመዘኑን፣ ማስረጃ ለመመዘን ሥልጣን ያለው መሆን አለመሆኑንና ግራቀኙ ያረጉትን ክርክር መሠረት ያደረገ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ አዟል፡፡ ተጠሪ በ10/04/2016 ዓ/ም በጻፈው መልስ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር መሠረት ማድረግ በሕግ ውሳኔ ሰጠ እንጂ ማስረጃ አመልዘነም፣ አስተዳደር ፍርድ ቤት በደንብ ቁጥር 155/2000 አንቀጽ 42 መሠረት ሊወሰን ሲገባ ተፈጻሚነት ያለውን ሕግ መሠረት ባለማድረጉ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይሕን በማረም የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው፡፡ አመልካች ከ08/01/2014 እስከ 23/04/2014 ዓ/ም ድረስ በሥራ ገበታቸው ላይ ባለመገኘታቸው ወደሥራ ቦታቸው ሊመለሱ አይገባም ተብሎ መወሰኑ ላይ የተፈጸመ ስህተት የለም ብሏል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ውሳኔው ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን ከግራቀኙ ክርክር፣ በሥር ፍርድ ቤት ከተረጋገጠው ፍሬ ነገርና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች ከመስከረም 08 ቀን 2014 ዓ/ም ጀምሮ በሥራ ገበታቸው ባለመገኘታቸው የተጠሪ መሥሪያ ቤት አዋሽ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሕዳር 09 ቀን 2014 ዓ/ም የሥራ ውላቸውን የማቋረጥ አስተዳደራዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ይግባኝ ያቀረቡት በዚህ ወሳኔ ላይ አይደለም፣ አመልካች ታህሳስ 23 ቀን 2014 ዓ/ም ለተጠሪ ዋና መሥሪያ ቤት ቅሬታ ያቀረቡ ሲሆን ጥር 25 ቀን 2014 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ አመልካች በደንብ ቁጥር 155/2000 አንቀጽ 42(1) መሠረት ከሥራ ቦታቸው ከቀሩ በሦስት ወር ውስጥ ለመመለስ ያላመለከቱ በመሆኑ ወደሥራቸው ሊመለሱ አይገባም በማለት አስተዳደራዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በመሥሪያ ቤቱ የተዘረጋው የቅሬታ አሰማም ሥርዓት ተከትሎ አመልካች ይግባኝ ያቀረቡት በዚህ የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ላይ በመሆኑ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይሕን መሠረት አድርጎ ጉዳዩን መመርመሩ ሕጉን የተከተለ ነው፡፡

አመልካች በፌደራል መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 መሰረት ተጠሪ ወደስራ ሊመልሰኝ ይገባል በሚል የሚከራከሩ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ የአመልካች ወደስራ የመመለስ ጥያቄ በመስሪያቤቱ የሠራተኞች አስተዳደር ደንብ ቁጥር 155/2000 አንቀጽ 42 መሰረት በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ወደስራ ለመመለስ ያልጠየቀ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ ይሕም ጉዳዩ የሚገዛበት ሕግ ላይ ግራ ቀኙ የክርክር ልዩነት ያላቸው መሆኑን ያሳያል፡፡ በፌደራል መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 የተፈጻሚነት ወሰኑ በአንቀጽ 4 እንደተመለከተው በመንግስት መሥሪያ ቤትና በመንግስት ሠራተኞች ላይ ነው፡፡ በመርሕ ደረጃ ማንኛውም የፌደራል የመንግስተ ሠራተኛ የሚተዳደረው በዚሁ ሕግ መሠረት ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል ሕግ አውጪው ሲፈቅድና በተለየ ሕግ ሲደነገግ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ሠራተኞቻቸውን በተለየ ሕግ ሊያስተዳድሩ ይችላሉ፡፡ የፌደራል የገቢዎች ባለስልጣንን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 587/2000 አንቀጽ 19/1/ለ የባለስልጣኑ ሠራተኞች የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣው ደንብ መሠረት እንደሚያስተዳድር ተመልክቷል፡፡ ይህን ተከትሎም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 155/2000 /በደንብ ቁጥር 408/2009 እንደተሻሻለ/ የተደነገገ ሲሆን ሠራተኞቹን የሚተዳደሩበትን ዝርዝር ድንጋጌዎች ይዟል፡፡ በደንብ ቁጥር 155/2000 አንቀጽ 44(1) ላይ የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ተፈጻሚነቱ በደንቡ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ የጉምሩክ ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 587/2000 ን የተካው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 437/2011 ተጠሪ ሠራተኞቹን በደንብ ቁጥር 155/2000 መሰረት ማስተዳደሩን የሚቀጥል መሆኑን ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ መሥሪያ ቤት ሠራተኞቹን የሚያስተዳድረው በፌደራል መንግስት ሠራተኞች አዋጅ መሰረት ሳይሆን በተለየ ሕግ ስለመሆኑ ያሳያል፡፡ በሰበር መዝገብ ቁጥር 225811 ላይ ተፈጻሚነት ያለው ሕግ የደንብ ቁጥር 155/2000 ስለመሆኑ ትርጉም የተሰጠበት ነው፡፡

በደንብ ቁጥር 155/2000 አንቀጽ 42(1) ላይ ማንኛውም ሠራተኛ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከሦስት ወር በላይ ከሥራ ተለይቶ የቆየ እንደሆነ አገልግሎቱ ሊቋረጥ እንደሚችል የተመለከተ ሲሆን በንዑስ ቁጥር ሁለት ላይ ደግሞ በሕመም ፈቃድ ከሥራ የተለዩትን ሠራተኞች የማይጨምር ስለመሆኑ ተገልጿል፤ በተያዘው ጉዳይ አመልካች ከመስከረም 08 ቀን 2014 ዓ/ም ጀምሮ ከሦስት ወር በላይ በሥራ ገበታቸው ያልተገኙ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡ አመልካች በሕመም ምክንያት የቀሩት ለሰባት ቀናት ብቻ በመሆኑ በደንቡ አንቀጽ 42(2) የተመለከተው ብቸኛው ልዩ ሁኔታ የሆነው በሕመም መቅረት የሚለው ተፈጻሚ ሊሆን አይችልም፡፡ አመልካች ወደሥራ ገበታቸው ያልተመለሱት በጦርነት ምክንያት መሆኑ በሥር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠነው፤ በደንብ ቁጥር 155/2000 አንቀጽ 42(1) መሠረት ከአቅም በላይ ሆኑ ምክንያቶች /ጦርነት ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ውስጥ የሚካተት ነው/ ከሥራ አለመገኘት ወደሥራ ሊያስመልስ የሚችል ምክንያት ነው፤ ሠራተኛው የደረሰበት ችግር ከእርሱ አቅም በላይ የሆነ ምክንያት በመሆኑ የስራ ዋስትናው እንዲከበር ሕጉ ዓላማ ያለው መሆኑን ያሳያል፤ በሌላ በኩል አሠሪው የሥራ መደቡን ለምን ያሕል ጊዜ ክፍት አድርጎ ይጠብቃል የሚለው ደግሞ የሕዝብ ጥቅም መሠረት በማድረግ

በሦስት ወር ጊዜ መገደቡ ሕግ አውጪው ሁለቱን ተነጻጻሪ ጥቅሞች ለማስታረቅ የወሰደው የፖሊሲ ውሳኔ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ስለሆነም ሠራተኛው ከሦስት ወራት በላይ ከስራ ገበታው ውጭ ከቆየ የሥራ አገልግሎቱን የማቋረጥ መብት ለአሠሪው መሥሪያ ቤት ሕጉ የሰጠ በመሆኑ ተጠሪ ይሕን ሕግ መሠረት በማድረግ የአመልካችን ወደሥራ ልመለስ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ ሆነ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች ወደሥራ ሊመለሱ አይገባም በማለት መወሰኑ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አላገኘንበትም፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 230062 ግንቦት 29 ቀን 2015 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ አንቀጽ 17/2015 አንቀጽ 9(1)(ሀ) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

- ❖ የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- ❖ ውሳኔው ሕዳር 04 ቀን 2017 ዓ/ም በችሎት ተነቧል፡፡
- ❖ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

<u>ማስታወሻ</u>፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

የሰበር መዝገብ ቁጥር 252651

ጥቅምት 8 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች:- እትመት አሠፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች:- 1ኛ. ወ/ሮ መቅደስ አያሌው - 2ኛ አመልካች ወኪል ቀርቧል

2ኛ. ወ/ሪት ሂሩት ተፈራ - ቀርቧል

ተጠሪዎች:-1ኛ. አቶ ደምሰው ተፈራ - ቀርቧል

2ኛ. አቶ ሲሳይ ተፈራ የ2ኛ 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ተወካይ 1ኛ ተጠሪ ቀርቧል

3ኛ. አቶ አስቻለው ተፈራ

4ኛ. አቶ ገዛኸኝ ተፈራ

5ኛ. አቶ ግሩም አብዶሽ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ጉዳዩ የውርስ ንብረት ክፍፍልን የሚመለከት ሲሆን ክሱ በቀረበበት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካቾች ተከሳሾች፣ተጠሪዎች ደግሞ ከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- የሟች አባታቸው አቶ ተፈራ አባይሮም እና የሟች እናታቸው ወ/ሮ እናኑ ታገለ የውርስ ሀብት ተጣርቶ በመዝገብ ቁጥር 57686 የካቲት 13 ቀን 2012 ዓ.ም በፀደቀው የውርስ አጣሪ ሪፖርት መሰረት በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 02 ውስጥ የሚገኘው የቤት ቁጥሩ 1052/7 የሆነው መኖሪያ ቤት እና ይዞታ ላይ የተገነባው ዋናው ቤት እና 03 ክፍል ሰርቪስ ቤቶች የሟቾቹ ወላጆቻቸው አቶ ተፈራ አባይሮም እና ወ/ሮ እናኑ ታገለ በጋብቻ ጊዜ በጋራ ያፈሩት የውርስ ንብረት መሆኑ ተጣርቶ ከሟች አባታቸው ድርሻ ላይ ተጠሪዎች እና 2ኛ አመልካች እያንዳንዳችን 1/6ኛ ድርሻ፣እንዲሁም ከሟች እናታታቸው ድርሻ ተጠሪዎች እያንዳንዳቸው 1/5ኛ ድርሻ ያላቸው መሆኑን ፣ ከዋናው መኖሪያ ቤት እና 03 ክፍል ሰርቪስ ቤቶች ፣እንዲሁም 1ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በግል ገንዘባቸው ከሰሯቸው ቤቶች ውጭ ያሉት ሰርቪስ ቤቶች ግማሹ የተጠሪዎች እና የ2ኛ አመልካች ድርሻ ሲሆን 1ኛ አመልካችም ግማሽ ባለድርሻ ናቸው፡፡ 1ኛ አመልካች እነዚህን ቤቶች በማከራየት የሰበሰቡት የኪራይ ገቢ ከየካቲት 13 ቀን 2012 ዓ.ም በኋላ ያለው የ31 ወር በድምሩ 179,800.00(አንድ መቶ ሰባ ዘጠኝ ሺ ስምንት መቶ) በግላቸው እየተጠቀሙት እንደሚገኙ በመግለጽ የኪራዩ ገንዘብ ከነወለዱ ፣እንዲሁም ዋናውን ቤት እና ሰርቪስ ቤቶቹን የአመልካቾችን ድርሻ እንዲያካፍሏቸው እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡

አመልካቾችም ለክሱ በሰጡት መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክር ያቀረቡ ሲሆን በፍሬ ነገር ክርክራቸው የካቲት 13 ቀን 2012 ዓ.ም በመዝገብ ቁጥር 57686 በጸደቀው የውርስ አጣሪ ሪፖርት መሰረት የተጠሪዎች እናት በቤቱ ላይ ያላቸው ድርሻ ዋናው ቤት ላይ ብቻ ሲሆን 1ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በግል ከሠሯቸው ቤቶች ውጭ ያሉት ሰርቪስ ቤቶች እና የኪራይ ገቢው ግማሽ ድርሻ የ1ኛ አመልካች መሆኑ ተወስኗል፡፡ በውሳኔ መሠረት 1ኛ አመልካች 50% ባለድርሻ የሆኑት በ11 ክፍል ሰርቪስ ቤቶች ላይ እንጅ በ3 ክፍል ሰርቪስ ቤቶች ላይ አይደለም፡፡ የኪራይ ገንዘቡን 5,800.00(አምስት ሺ ስምንት መቶ) ከየካቲት 5 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ነሃሴ 13 ቀን 2012 ዓ.ም ድረስ ያለውን 50% የተጠሪዎችን ድርሻ ለማካፈል ፈቃደኛ መሆናቸውን ገልጸው በይዞታው ላይ ካሉት 13 ክፍል ሰርቪስ ቤቶች ውስጥ 50% ድርሻቸው እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ በሰጠው ውሳኔ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 02 ውስጥ የሚገኘው የቤት ቁጥር 1052/7 ዋናው ቤት ከ3 ክፍል ሰርቪስ ቤቶች ጋር የተጠሪዎች አባት እና እናት መሆኑ በውርስ ማጣራቱ ድምዳሜ የተደረሰበት በመሆኑና አመልካቾችም የተጠሪዎችን የውርስ ድርሻ ለማካፈል ክደው ስላልተከራካሩ ተጠሪዎች ከዋናው ቤት እና 3 ክፍል ሰርቪስ ቤቶች የእናታቸው ድርሻ 1/5ኛ ፣ የአባታቸውን ድርሻ ከሟች እናታቸው እና ከ1ኛ አመልካች ጋር ካፈሩት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ውስጥ ድርሻቸው 1/6ኛ መሆኑን፤ የቤት ኪራዩ የ31 ወራት ስሌቱ ብር 179,800.00 /አንድ መቶ ሰባ ዘጠኝ ሺ ስምንት መቶ/ መሆኑን ጠቅሶ 50 በመቶ የውርስ ሀብት በመሆኑ ተጠሪዎች እና 2ኛ አመልካች 1/6ኛ ድርሻቸውን በሕጉ በተመለከተው አግባብ እንዲካፈሉ በፍርዱ የተመለከተ ሲሆን የቤት ኪራዩ በወር 5,800.00(አምስት ሺ ስምንት መቶ) የ31 ወራት ብር179,800.00 /አንድ መቶ ሰባ ዘጠኝ ሺ ስምንት መቶ/ 1/6ኛ ድርሻ ለእያንዳንዳቸው 29,666.67(ሃያ ዘጠኝ ሺ ስድስት መቶ ስልሳ ስድስት ሺ ከ67/100) በአጠቃላይ 149,833.33(አንድ መቶ አርባ ዘጠኝ ሺ ስምንት መቶ ስልሳ ሶስት ከ33/100) 1ኛ አመልካች እንዲከፈሉ ወስኗል፡፡ አመልካቾች ይሕን ውሳኔ በመቃወም ያቀረቡት የይግባኝ አቤቱታ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዟል፡፡

የሰበር ቅሬታው የቀረበው በሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል በሰበር ለማስለወጥ ሆኖ የቅሬታው ይዘት በአጭሩ፡- በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 02 ውስጥ የሚገኘው የቤት ቁጥሩ 1052/7 የሆነው መኖሪያ ቤት ዋናው ቤት፤እንዲሁም 1ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በግል ከሰሯቸው ሰርቪስ ክፍል ቤቶች ውጭ ባሉት ሰርቪስ ቤቶች ላይ 1ኛ አመልካች ግማሽ ባለድርሻ መሆናቸው በመዝገብ ቁጥር 57686 የካቲት13 ቀን 2012 ዓ.ም ተሻሽሎ በፀደቀው እና እስከ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት ድረስ ክርክር ተደርጎበት ከፀናው የውርስ አጣሪ ሪፖርት በተቃራኒ 03 ክፍል ሰርቪስ ቤቶች የሚኖቹ አቶ ተፈራ አባይሮም እና ወ/ሮ እናኑ ታገለ ነው በማለት የድርሻ ክፍፍል ውሳኔ መሰጠቱ የ1ኛ አመልካችን የንብረት ባለቤትነት መብት ስለሚጥስ 1ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በግል ከሰሯቸው ሁለት ክፍል ሰርቪስ ቤቶች ውጭ ያሉት 10 ክፍል (ጠቅላላ) ሰርቪስ ቤቶች 50% የ1ኛ አመልካች ድርሻ ነው ተብሎ እንዲወሰን ጠይቀዋል፡፡ በግቢው ውስጥ ከ10 -13 ክፍል ሰርቪስ ቤቶች መኖራቸው እየታወቀ 1ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የሰሯቸው ቤቶች የትኞቹ እንደሆኑና ብዛታቸው በግልጽ ተለይቶ ውሳኔ አለመሰጠቱ በአፈፃፀም ላይ ውዝግብ ስለሚያስነሳ ተለይቶ ውሳኔ እንዲሰጥ ጠይቀዋል፡፡ ከቤት ኪራይ የተገኘው ገቢ ግማሹ የ1ኛ አመልካች ሆኖ ቀሪው የሟች አቶ ተፈራ አባይሮም ወራሾች ሆኖእያለ የሚስትነት ድርሻቸውን በማሳጣት ሙሉ በሙሉ የሟች ወራሾች እንዲካፈሉት ውሳኔ መስጠቱ ፤ 4ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች የልጅ ልጆች /የሟች የወ/ሮ መነን ተፈራ/ ልጆች በመሆናቸው በጋራ አንድ እጅ ሊያገኙ ሲገባ የ2ኛ አመልካችን 1/5ኛ የማግኘት መብት በጣሰ መልኩ ሁለቱ እያንዳንዳቸው ለየብቻ 1/6ኛ ባለድርሻ እንደሆኑ ተደርጎ መወሰኑ ፤ ተጠሪዎች በስር ፍርድ ቤት የድርሻ ክፍፍል እንድንከፋፈል ክስ ከማቅረባቸው በፊት ቅድመ ማስጠንቀቂያ ባልሰጡበት እና አመልካቾችም ትክክለኛውን የውርስ ድርሻ መጠን አናካፍልም ብለው ባልተከራከሩበት፤ እንዲሁም ክርክራቸው ክፍፍሉ መሆን ያለበት የውርስ አጣሪ ሪፖርቱን መሠረት አድርጎ ነው የሚል ሆኖእያለ ተጠሪዎች ያለአግባብ ከድርሻቸው በላይ ግልጽነት በጎደለው ሁኔታ አመልካቾችን ከሰው ለወጪ በዳረጉበት ሁኔታ ከወጭና ኪሣራ ድንጋጌ መርህ ውጭ አመልካቾች

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ለተጠሪዎች ወጭና ኪሣራ 10 (አስር) ሺህ ብር እንድንከፍል የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት መሆኑን ጠቅሰው የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲሻር ጠይቀዋል፡፡

በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 6(1) መሠረት ለሰበር ሰሚው ችሎቱ የተመራው አቤቱታ በሰበር ሰሚ ችሎቱ ተመርምሮ የውርስ ክፍፍል ክርክር በዋነኛነት መመራት ያለበት ውርስ ማጣራት ውጤትን መሠረት አድርጎ ከመሆኑ አኳያ ክርክር ባስነሳው ቤት ያሉ ሰርቪስ ቤቶች የተጠሪዎች እናት በከፊል መብት ያላቸው መሆኑ ፣1ኛ አመልካች መብት ያላቸው በውስን ሰርቪስ ቤቶች ላይ ብቻ ነው መባሉ በመዝገብ ቁጥር 57686 የፀደቀው የውርስ አጣሪ ሪፖርትን መሠረት ያደረገ መሆን አለመሆኑን ፣ እንዲሁም 4ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች በውርስ ማጣራት ሪፖርቱ ላይ ያላቸው ድርሻ እና በክፍፍል ውሳኔ ላይ ድርሻቸው መለያየቱ ሕጋዊ መሆን አለመሆኑን፣ የቤት ኪራን በተመለከተ በውርስ ማጣራቱ ወቅት የ1ኛ አመልካች ደርሻ ነው ተብሎ ከተመለከተው አንፃር የ1ኛ አመልካች የድርሻ መጠን የተጠበቀላቸው መሆን አለመሆኑን ከቤተሰብ ሕጉ እና ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ - መንግስት አንቀጽ 40 ሥር የተመለከተውን የንብረት መብት ያከበረ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪዎች ተከታዩን መልስ ሰጥተዋል፡፡

ተጠሪዎች የፍርድ ቤቱ መጥሪያ ደርሷቸው ለሰበር አቤቱታው በሰጡት መልስ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 2 በቤት ቁጥር 1052/7 ተመዝግቦ የሚገኘው ዋናው ቤት 3 ክፍል በአንድ ጣራ ስር የሆነው ፣ መፀዳጃ ቤት ፣ ዕቃ ቤት እና ማዕድ ቤት በአንድነት ተያይዞ የሚገኘው በሟች እናታቸው እና ሟች አባታቸው የተሰራ የጋራ ንብረት በመሆኑ የውርስ ሀብት ድርሻቸ ነው፡፡ በሟች ወላጆቻችን ይዞታ ውስጥ 1ኛ፣2ኛ ፣3ኛ ተጠሪዎች እንደቅደም ተከተላቸው 1ኛ ተጠሪ አንድ ክፍል ቤት ፣ 2ኛ ተጠሪ ሁለት ክፍል ቤት ፣ 3ኛ ተጠሪ አንድ ክፍል ቤት በራሳቸው ገንዘብ ማንም ሳይቃወማቸው ሰርተው ትዳር መስርተው ልጆች ወልደው እየኖሩበት ያሉ ቢሆንም 1ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የሰሩት ቤት ብቻ የግል ንብረት ነው ተብሎ መወሰኑ ፣1ኛ አመልካች ከሟች አባታቸው ጋር በኖሩበት ጊዜ የተሰሩት ሰርቪስ ቤቶች በ2ኛ ተጠሪ የተሰሩት ሁለት ክፍል ቤቶች እንዲሁም ተጨማሪ ሁለት ክፍል ሰርቪስ ቤቶች 1ኛ አመልካች እና ሟች አቶ ተፈራ አባይሮም በትዳር ውስጥ እያሉ የተሰሩ ናቸው ተብሎ ውሳኔ በመሰጠቱ የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም፡፡ በሟች የተጠሪዎች እናት እና በሟች አባታቸው የተሰሩ ቤቶች ጭምር በወር ብር 5,800 (አምስት ሺህ ስምንት መቶ ብር) ቢከራዩም የተጠሪዎች ድርሻ ያልተሰጣቸው መሆኑን፣4ኛ እና 5ኛ ተራቁጥር ላይ የተመለከቱት ተጠሪዎች የሚቿ ወ/ሮ መነን ተፈራ ልጆች እና የሟች እናታቸው ተተኪ ወራሾች ስለሆኑ የእናታቸውን የውርስ ድርሻ እንዲካፈሉ ቢደረግ ተቃውሞ እንደሌላቸው ገልፀዋል፡፡

አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ከዚህ በላይ አጠር ባለ መልኩ የተመለከተው የግራ ቀኝ ክርክር እና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ውሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ሲል የያዘውን ጭብጥ እና በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለው ሕግ፤እንዲሁም በጉዳዩ ላይ ከተሰጠው አስገዳጅ የሰበር ውሳኔ አንፃር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የውርስ ማጣራት ተግባር ዋና ዓለማው የሟችን ንብረት ማጣራት እና መፈለግ ፣ ከሟች ንብረት መብት አለን ባዮችን ወይንም ወራሾችን መወሰን ፤ በኑዛዜው መሠረት ተጠቃሚዎችን መለየት ፤ የኑዛዜ ስጦታዎችንና ዕዳ መክፈል እና የውርስ ሀብቱን ማስተዳደር መሆኑን ከፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 944 እና 956 ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል። ውርስ ከተጣራ በኋላ የውርስ አጣሪው ሪፖርት ለወራሾች እና ፍርድ ቤት መቅረብ እንዳለበት የፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 960 ድንጋጌ ያመለክታል፡፡ ተጣርቶ የቀረበውን የውርስ አጣሪ ሪፖርት መሠረት በማድረግ ወራሾች የወራሽነት የምስክር ወረቀት ከፍርድ ቤት ማግኘት የሚችሉ መሆኑን የፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 996 ያስገነዝበናል። በወራሽነት የምስክር ወረቀት በተመለከተው አግባብ ወራሾች የውርስ ድርሻ ክፍፍል መጠየቅ የሚችሉ መሆኑን የፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 1062 ያስረዳናል። በክፍፍል ረገድ አለመግባባት ቢፈጠር የወራሽነት የምስክር ወረቀቱ ክሱን ለማቅረብ መብት ወይንም ጥቅም የሚሰጣቸው በመሆኑ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክስ ለማቅረብ ይችላሉ። በሌላ በኩል በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 999 በተደነገገው መሠረት አንድ ሰው ዋጋ ያለው የወራሽነት ማስረጃ ሳይኖረው ውርሱን ወይንም ከውርሱ አንዱን ክፍል በእጁ ያደረገ እንደሆነ እውነተኛ ወራሽነቱ እንዲታወቅለት የተወሰደበት የውርስ ሀብት እንዲመለስለት የወራሽነት ጥያቄ ክስ ለማቅረብ እንደሚችል ተመክቷል። በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 996/1 መሠረት የሚሰጥ የወራሽነት የምስክር ወረቀት ለሟቹ ወራሽ የሆነውን ሰው እና ከውርሱ የሚያገኘውን ድርሻ የሚያመለክት ማስረጃ ነው።

የወራሽነት የምስክር ወረቀት የውርስ ድርሻ ክፍፍል ጥያቄ ለማቅረብ መብት እና ጥቅም ያለው መሆኑን ለማሳየት በማስረጃነት እንደምቀርብ የሰበር ሰሚ ችሎቱ በሰበር መዝገብ ቁጥር 18576 እና 45905 ላይ አስገዳጅ ውሳኔን ሰጥቷል፡፡ የውርስ አጣሪ ሪፖርት ከማስረጃት በዘለለ እራሱን ችሎ መብት የማያጎናጽፍ ባለመሆኑ በክፍፍል ጊዜም ቢሆን የማስረጃውን ቅቡልነት ፤ ተገቢነት ፤ ተአማንነት እና የመሳሰሉት መቃወሚያዎች ሊቀርብበት ይችላል፡፡ አስገዳጅ የሰበር ትርጉሙ በዋናነት ታሳቢ የሚያደርገው የውርስ ንብረት ክፍፍል ጥያቄ ሲቀርብ አስቀድሞ ውርሱ በሚጣራበት ወቅት በተጣራው የውርስ ንብረት ላይ ተገቢውን መከራከሪያ አቅርቦ ክርክሩ ተቀባይነት ያላገኘን ወይንም በውርስ ማጣራቱ ወቅት ተገቢውን መከራከሪ ማቅረብ ሲገባው ያላቀረበ ተከራካሪ ተጨማሪ ዕድል በመስጠት የውርስ ማጣራቱን ተግባር ዋጋ ለማሳጣት ታስቦ ሳይሆን ውርስ ሲጣራ ያልነበረ ሰው መብት እና ጥቅም ጥበቃ ለማድረግ ታስቦ እንጅ በውርስ አጣሪ ሪፖርቱ አምኖ ማስረጃውን ያወጣው

ወገን ሃሳቡን በቀየረ ቁጥር የቀደመውን ማስረጃ በሌላ ማስረጃ በማስተባበል ዋጋ ማሳጣት ክርክሩ ማቆሚያ እንዲያጣ ማድረግ የህጉ ዓላማ አይደለም። ግራ ቀኙ በተገኙበት ክርክር ተደርጎና ማስረጃ ተሰምቶ የፀደቀ የውርስ አጣሪ ሪፖርት ተከራካሪዎቹ ላይ አስገዳጅነትና ተፈፃሚነት ያለው በመሆኑ እንደመጨረሻ ውሳኔ አይቆጠርም ሊባል እንደማይችል የሰበር ሰሚ ችሎቱ በሰበር መዝገብ ቁጥር 225388 ላይ አስገዳጅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አንድ ሰው ኑዛዜ ሳያተርፍ የሞተ እንደሆነ የውርስ ሀብቱ በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 842 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች አግባብ እንደምተላለፍ ተመልክቷል። በዚህ መሰረት የሟች ልጆች የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች መሆናቸውንና በወራሽነታቸውም ከውርስ ሀብቱ እያንዳንዳቸው ትክክል (እኩል) ድርሻን እንደምቀበሉ ተጠቃሹ ድንጋጌ ያመለክታል፡፡ የውርስ ንብረት ክፍፍል የሚደረግበት መንገድ በፍትሐ ብሔር ህጉ ተመልክቷል፡፡ የውርስ ንብረት ክፍፍል አሰራር በወራሾች መካከል በሚደረግ ስምምነት፤ ወራሾች ያልተስማሙ እንደሆነ ከእነርሱ መካከል አንዱ ተግቶ ያሰናዳው የክፍያ ሐሳብ እንዲፀድቅ ለዳኞች ቀርቦ በሚጸድቀው አግባብ ሊከናወን እንደሚችል የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1079 ይደነግጋል፡፡ የመከፋፈሉን አፈፃፀም በተመለከተም የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር1082 ክፍያው የሚፈፀመው ሟቹ በፃፈው የኑዛዜ ቃል መሰረት እንደሆነ፤ ስለክፍያው አፈፃፀም የተፃፈ ኑዛዜ ቃል ከሌለ ደግሞ በሕጉ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት መደረግ እንዳለበት ተመልክቷል፡፡ የውርስ ንብረት ክፍፍል በውርስ ሕጉ ክፍፍልን የሚገዙ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የተከተለ እና ያገናዘበ መሆን እንዳለበት በሰበር መዝገብ ቁጥር 94322(በቅጽ 16 እንደታተመው) አስገዳጅ ውሳኔ ተስጥቷል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ለክርክሩ መነሻ በሆነው ቤት ውስጥ 1ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በራሳቸው ወጪ በሟች አቶ ተፈራ አባይሮም ፈቃድ የሰሩት ቤቶች በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1179 መሰረት የውርስ ሀብት ሊሆኑ እንደማይገባ ፤ የሟች አቶ ተፈራ አባይሮም ሚስት የነበሩት 1ኛ አመልካች ክርክር ያስነሳውን ዋናውን ቤት ከሟች ጋር በጋራ ያላፈሩ መሆኑን ፤ ዋናው ቤት የተፈራው ሟች አቶ ተፈራ አባይሮም እና በሟች ሚስታቸው ከወ/ሮ እናኑ ታገለ መሆኑን፤1ኛ አመልካች እና የተጠሪዎች ወላጅ አባት በትዳር ውስጥ እያሉ ዋናውን ቤት የጋራ የሚያስብል ዕድሳት እና ግንባታ ስላላተደረገ ዋናው ቤት የተጠሪዎች ወላጆች(ሟች አቶ ተፈራ አባይሮም እና የሟች ወ/ሮ እናኑ ታገለ) የጋራ ሀብት በመሆኑ ተጠሪዎች እያንዳንዳቸው 1/5ኛ ባለድርሻ መሆናቸውን ፤1ኛ አመልካች እና ሟች አቶ ተፈራ አባይሮም በትዳር አብረው ሲኖሩ አዲስ የሰሯቸው 1ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ከሰሯቸው ቤቶች ውጪ የሖኑ ቤቶች እንዳሉ እና እነዚህ ቤቶች የሟቹ አቶ ተፈራ አባይሮም እና የ1ኛ አመልካች ስለሆኑ 50% የ1ኛ አመልካች ድርሻ ከተለየ በኋላ ቀሪው የውርስ ሀብት መሆኑን ፤ ከቤት ኪራይ በወር ከሚገኘው 5,800.00 /አምስት ሽህ ስምንት መቶ ብር/ ውስጥ ግማሹ ማለትም 2,900.00 (ሁለት ሺ

ዘጠኝ መቶ) የአመልካች ሆኖ ቀሪው ግማሽ ደግሞ የውርስ ሀብት መሆኑን ፤ ከ1ኛ- 3ኛ ያሉት ተጠሪዎች እና 2ኛ አመልካች የሟች አቶ ተፈራ አባይሮም ልጆች እና የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች ስለሆኑ የሟች የውርስ ሀብት ከሆኑት ቤቶች እና ከቤት ኪራይ ገቢው እያንዳንዳቸው 1/5ኛ ድርሻ እንዳላቸው ፤ እንዲሁም 4ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች የሟች ወ/ሮ መነን ተፈራ ልጆች ፤ የሟች አቶ ተፈራ አባይሮም የልጅ ልጆች እና ተተኪ ወራሾች ስለሆኑ የውርስ ሀብቱን 1/5ኛ ድርሻ እኩል እንዲካፈሉ፤እንዲሁም1ኛ አመልካችም ከሟች ጋር ያፈሯቸውን ሰርቪስ ቤቶች እና የኪራይ ገንዘብ ግማሽ ባለድርሻ ናቸው በማለት የውርስ አጣሪው ሪፖርቱን በማሻሻል የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የካቲት 13 ቀን 2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት በመዝገብ ቁጥር 57686 የሰጠው ውሳኔ የሰበር ሰሚ ችሎቱ በሰበር መዝገብ ቁጥር 206713 አጽናቷል፡፡

ለውርስ ሀብት ክፍፍል መሠረቱ የውርስ ማጣራት ሆኖእያለ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 02 ውስጥ የሚገኘው የቤት ቁጥሩ 1052/7 ከሆነው ዋናው ቤት ፤ እንዲሁም በ1ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የግል ንብረት ናቸው ከተባሉት ሰርቪስ ቤቶች ውጪ ያሉት ሰርቪስ ቤቶች የተጠሪዎች እና የ2ኛ አመልካች አባት የሆኑት ሟች አቶ ተፈራ አባይሮም እና 1ኛ አመልካች መሆኑ በውርስ ማጣራት ሪፖርቱ ተረጋግጦ ተሸሽሎ የፀደቀው የውርስ አጣሪ ሪፖርት ላይ ክርክር ተደርጎ በሰበር መዝገብ ቁጥር 206713 ፀንቶ ካለው የውርስ ማጣራት ሪፖርት በተቃራኒ 1ኛ አመልካች የ3 ክፍል ሰርቪስ ቤቶች ግማሽ ባለድርሻ ናቸው መባሉ፤ 179,800.00 /አንድ መቶ ሰባ ዘጠኝ ሺ ስምንት መቶ/ ብር ከሆነው የ31 ወራት የቤት ኪራይ 1ኛ አመልካች 50 በመቶ ባለድርሻ መሆናቸው በፍርዱ ውስጥ የተጠቀሰ ቢሆንም 1ኛ አመልካችን እንደ አንድ ወራሽ በመቁጠር 149,833.33(አንድ መቶ አርባ ዘጠኝ ሺ ስምንት መቶ ስልሳ ሶስት ከ33/100) ለወራሾች እንዲያካፈሉ መወሰኑ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 90 መሰረት 1ኛ አመልካች ከሟች ባለቤታቸው አቶ ተፈራ አባይሮም ጋር በትዳር ውስጥ ያፈሩትን ንብረት በሕጉ በተቀመጠው የክፍፍል ሥርዓት መሠረት እኩል የመካፈል መብታቸውን ፤ ለዜጎች ሁሉ የኢ.ፌዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40/1 እኩል ጥበቃ የተደረገለትን የግል ንብረት የማፍራት መሠረታዊ መብት ፤ እንዲሁም ከሁሉም የንብረት መብቶች የሰፋ በሕግ ብቻ የሚገደበውን በፍትሐ ብሔር ህጉ ቁጥር 1204 እና 1205 ሥር የተመለከተውን ባለሀብትነትን በሚገድብ መልኩ እና በሕገ-መንግስቱ የተረጋገጡ መብቶች እና ጥበቃዎች በመጠቀም ረገድ ሴቶች ከወንዶች እኩል መብት እንዳላቸው የሚደነግገውን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ - መንግስት አንቀጽ 35/1 ይጥሳል፡፡ 4ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች የሟች ወ/ሮ መነን ተፈራ ልጆች ፤ የሟች አቶ ተፈራ አባይሮም የልጅ ልጆች እና ተተኪ ወራሾች ስለሆኑ የውርስ ሀብቱን 1/5ኛ ድርሻ እኩል እንዲካፈሉ ሊወሰን ሲገባው ከቀሪዎቹ የሟች አቶ ተፈራ አባይሮም ልጆች(የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች) እኩል1/6ኛ ድርሻ እንዲያገኙ መወሰኑ 2ኛ አመልካች በሕጉ ማግኘት የሚገባቸውን የውርስ ድርሻ የሚያሳጣ የፍትሐ ብሔር ሕጉን ቁጥር 842 ድንጋጌን ይቃረናል፡፡ በአጠቃላይ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተያዘው ጉዳይ ላይ ያስተላላፈው ውሳኔ በፍርድ ሀተታው ውስጥ የተመለከቱትን

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የኢ.ፌዲ.ሪ ሕገ መንግስት ፤ የተሻሻለውን የቤተሰብ ህግ እና የፍትሐ ብሔር ሕጉን ድንጋጌዎችን ፤ እንዲሁም በጉዳዩ ላይ የተሰጠውን አስገዳጅ ውሳኔን የሚቃረን ሆኖእያለ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይሕን ውሳኔ በመቃወም የቀረበለትን የይግባኝ አቤቱታ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሰረት መሰረዙ መሠረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ ቀጣዩ ተወስኗል፡፡

**ውሳኔ**

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 305746 ግንቦት 24 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ብይን ፣ እንዲሁም የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 89629 ህዳር 30 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ ፣ ውሳኔ እና ትዕዛዝ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ - ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 9(1/ለ) መሠረት **ተሻሽሏል፡፡**
2. በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 02 ውስጥ የሚገኘው የቤት ቁጥር 1052/7 ዋናው ቤት ፤ በ1ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የተሰሩ የተጠሪዎቹ የግል ንብረት ናቸው ከተባሉት ሰርቪስ ቤቶች ውጪ ያሉት ሰርቪስ ቤቶች 1ኛ አመልካች ከተጠሪዎች እና 2ኛ አመልካች አባት ከሆነት ከአቶ ተፈራ አባይሮም ጋር በጋራ ያፈሩት በመሆኑ 1ኛ አመልካች ግማሽ ባለድርሻ ሲሆኑ ቀሪው ግማሽ የውርስ ሀብት ተብሎ ተወስናል፡፡
3. 179,800.00 /አንድ መቶ ሰባ ዘጠኝ ሺ ስምንት መቶ/ ብር ከሆነው የ31 ወራት የቤት ኪራይ 1ኛ አመልካች 50 በመቶ ባለድርሻ ስለሆኑ ለሟች የአቶ ተፈራ አባይሮም ወራሾች ሊያካፍሉ የሚገባው 89,900(ሰማኒያ ዘጠኝ ሺ ዘጠኝ መቶ) ብር ብቻ ነው ብለናል፡፡
4. 4ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች ሟች ወ/ሮ መነን ተፈራን ተክተው ሟች አያታቸው አቶ ተፈራ አባይሮምን ስለሚወርሱ የሟች አቶ ተፈራ አባይሮም የውርስ ሀብት መሆኑ የተጣራውን ንብረት 1/6ኛ ለሁለት እኩል እንዲካፈሉ ተወስኗል፡፡
5. በውሳኔው ተራቁጥር 2-4 ከተመለከቱት ውጪ ያለው የውሳኔ ክፍል አልተነካም(ፀንቷል)፡፡
6. በመዝገቡ ላይ መስከረም 25 ቀን 2016 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
7. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የግላቸውን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ውሳኔ አግኝቶ ስለተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

**መ/ዐ**

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ.መ.ቁ 252706
ጥቅምት 07 ቀን 2017 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** እትመት አሠፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

ሐብታሙ እርቅይሁን

አመልካች፡- ዓለሙ ታደሰ ታዬ - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ ለምለም ታደሰ - ቀረቡ

2. አቶ ዘነበ ታደሰ ታዬ - ወኪል 1ኛ ተጠሪ ቀረቡ

3. ወ/ሮ ሀና ታደሰ ታዬ - ቀረቡ

4. አቶ ብርሃኑ ታደሰ ታዬ - ቀረቡ

መዝገቡ ለፍርድ የተቀጠረ ነው፡፡ በዚሁ አግባብ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካች ነሐሴ 24 ቀን 2015 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 183116 የካቲት 28 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ብይን፤ ይህንኑ ብይን በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 306516 የሰጠው ብይን መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ጉዳዩ ኑዛዜ ይፍረስልኝ በሚል የቀረበን ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካች ከሳሽ፣ የአሁን ከ1ኛ እስከ 3ኛ ያሉት ተጠሪዎች ተከሳሾች፣ የአሁን 4ኛ ተጠሪ ደግሞ ጣልቃገብ ነበሩ፡፡

የአሁን አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ሟች አቶ ታደሰ ታዬ ሠኔ 26 ቀን 2007 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ ይፍረስልኝ በሚል ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁን 4ኛ ተጠሪም ባቀረቡት የጣልቃገብነት ክርክር ተመሳሳይ አቤቱታ ያቀረቡ ስለመሆኑ ከመዝገቡ ጋር ተያየዞ የቀረበልን የውሳኔ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

የአሁን ከ1ኛ እስከ 3ኛ ያሉት ተጠሪዎች ለአመልካች በሰጡት መልስ ሟች ያደረጉት ኑዛዜ በውርስ ማጣራት ጊዜም ቀርቦ የነበረ እና ከዚያም በፊት ሟች አባታችን ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩ በኋላ ግንቦት 03 ቀን 2013 ዓ.ም በአርባ ሶስተኛው ቀን ኑዛዜውን ከፈረሙት ሽማግሌዎች ውስጥ ከአቶ ይመር ደምሴ የተቀበልነውን የኑዛዜ ወረቀት አመልካችን ከስራ ሲመጣ ቤት ውስጥ አሳውቀነዋል፣ በኑዛዜው በመስማማት በኑዛዜው መሠረት ወራሽነቱን ከፍርድ ቤት ለማውጣት ተጠይቆ በቀን 10/10/2013 ዓ.ም የልደት የምስክር ወረቀቱን ሰጥቶን 1ኛ ተጠሪ ተወካይ ሆኖ የኑዛዜ ተጠቃሚ ስለመሆኑ በፍርድ ቤት ከእኛ ጋር ተረጋግጧል፣ አመልካች ኑዛዜውን ካወቀበት ከግንቦት 03 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ በ 15 ቀናት ውስጥ ወይም በሶስት ወራት ውስጥ ያልተቃወመ በመሆኑ ጥያቄው በይርጋ ይታገዳል፣ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም፣ ክሱም የክስ ምክንያት የለውም፣ በኑዛዜው ያገኘነው ድርሻ እኩል 500 ብር ነው፣ በተሰጠው መኖሪያ ቤት ከውርስ ተነቅያለሁ በሚል ብቻ የሚጠይቁት ዳኝነት ተጠሪዎችን አይመለከትም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡

4ኛ ተጠሪን በሚመለከት በሰጡት መልስ ደግሞ 4ኛ ተጠሪ በመ.ቁ 172103 የሟች አባታችን የውርስ ሐብት ይጣራልን በሚል ባቀረቡት አቤቱታ ላይ ተጠሪዎች በ 2013 ዓ.ም ጣልቃ ገብተን አቤቱታ ስናቀርብ ኑዛዜውን በማስረጃነት አቅርበነዋል፣ ኑዛዜውን በፍርድ ቤቱም ሆነ በውርስ አጣሪው በኩል እንዲያውቁት ተደርገዋል፣ ኑዛዜውን ካወቁበት ጊዜ ጀምሮ በ 15 ቀን ወይም በሶስት ወር ውስጥ ያልተቃወሙ በመሆኑ ጥያቄአቸው በይርጋ ይታገዳል በማለት መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ግራቀኙን በመቃወሚያው ላይ ከሰማ በኋላ መርምሮ ተጠሪዎች አመልካችን ቤተሰብ በተሰበሰበበት ስለኑዛዜው አሳውቀነዋል ያሉ ቢሆንም ሕጉ በሚፈቅደው አግባብ ውርስ አጣሪ ባለበት ኑዛዜ በሚነበብበት ወቅት አመልካች የነበሩ ስለመሆናቸው ያሉት ነገር የለም፣ አመልካች ኑዛዜውን አወቅኩ ያሉት በመ.ቁ 172103 4ኛ ተጠሪ ባስከፈቱት የውርስ ማጣራት መዝገብ ላይ በቀረበው የውርስ አጣሪ ሪፖርት ላይ ስለመሆኑ ቢገልጹም በአንድ በኩል ለ1ኛ ተጠሪ በሰጡት የውክልና ሰነድ መነሻነት ተጠሪዋ በአዲስአበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 27223 አመልካችን ጨምሮ ሌሎች ወራሾች የኑዛዜ ወራሽ ስለመሆናቸው ሟች አደረጉ የተባሉትን ኑዛዜ በማቅረብ ስለማስወሰናቸው እና የወራሽነት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ሰርተፍኬት ስለመወሰዳቸው በአመልካች በኩል አልተካደም፤ በሌላቸው የውክልና ስልጣን ማስረጃውን አውጥተዋል ካሉም ይህን እስካላሻሩ ድረስ የኑዛዜውን መኖር በመ.ቁ 17223 አቤቱታ ካቀረቡበት ከቀን 11/10/2013 ዓ.ም ጀምሮ ያውቁ እንደነበር በቀን 15/10/2013 ከተሰጠው የፍርድ ቤቱ የወራሽነት ማስረጃ ላይ ማረጋገጥ ተችሏል፤ ከዚሁ በተጨማሪ 1ኛ ተጠሪ በመ.ቁ 172103 በነበረው የውርስ ማጣራት ጉዳይ ማስረጃውን እና ውክልናቸውን በመያዝ አመልካችን ጨምረው ጣልቃ ለመግባት አቤቱታ አቅርበው 4ኛ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ጣልቃእንዲገቡ ብይን ተሰጥቷል፤ አመልካችም የጣልቃገቡን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ከቀን 14/12/2013 ዓ.ም ጀምሮ የውርስ ማጣራቱ ይከናወንበት በነበረው የመ.ቁ 172103 በችሎት እየቀረቡ ጉዳዩን ሲከታተሉ ነበር፤ አመልካች ስለኑዛዜው መኖር ያወቁት በወኪላቸው አማካኝነት በቀን 11/10/2013 ዓ.ም በራሳቸው ደግሞ ከቀን 14/12/2013 ዓ.ም ጀምሮ ነው፤ አመልካች ኑዛዜው እንዲሻር ክስ ያቀረቡት በቀን 18/12/2014 ዓ.ም ነው፤ አመልካች የኑዛዜውን መኖር ካወቁ በኋላ በሕጉ በተቀመጠው 15 ቀን ውስጥ ኑዛዜው አይጸናም የሚሉበትን ምክንያት መግለጫ ያላቀረቡ በመሆኑ ጥያቄያቸው በይርጋ ቀሪ ነው፤ 4ኛ ተጠሪም ስለኑዛዜው ያወቁት ሲከራከሩበት በነበረው የመ.ቁ 172103 በሆነው መዝገብ ከ1ኛ እስከ 3ኛ ያሉት ተጠሪዎች በቀን 30/10/2013 ዓ.ም የጣልቃገብነት አቤቱታ ሲያቀርቡ በመሆኑ እና ኑዛዜውን በመቃወም የቀረቡት በቀን 15/03/2015 ዓ.ም በመሆኑ በሕጉ የተቀመጠው ጊዜ ካለፈ በኋላ ስለቀረቡ ጥያቄአቸው በይርጋ ይታገዳል በማለት በብይን ውድቅ አድርጎታል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት ይግባኛቸው ተሰርዟል፡፡

አመልካች ነሐሴ 24 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይህን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ሲሆን ይዘቱም፡- ኑዛዜው የሟች እናቴን ድርሻ ያጠቃለለ በወላጆቼ ፈቃድ የሰራሁትን ቤት ያካተተ ስለሆነ እንዲረፍስ ጠይቄአለሁ፤ አመልካች ከኑዛዜው ተነቅያለሁ፤ በኑዛዜው ላይ ያለው ፊርማ የአባቴ ፊርማ አይደለም፤ ለ1ኛ ተጠሪ ከእናቴ የማገኘውን የውርስ ሐብት በተመለከተ ግንቦት 13 ቀን 2010 ዓ.ም ውክልና ሰጥቻታለሁ፤ ከወላጅ አባቴ የሚገኘውን ውርስ በተመለከተ ምንም ዓይነት ውክልና አልሰጠኋትም፤ ባልተሰጣት ውክልና የኑዛዜ ወራሽነት ምስክር ወረቀት እንደተቀበለች በከፍተኛ ፍርድ ቤት አምናለች፤ የእናቴን ውርስ በሚመለከት ብቻ በሰጠሁት ውክልና በመ.ቁ 172103 ውርስ ሲጣራ ቆይቷል፤ በዚህ መዝገብ በቀን 14/12/2013 ዓ.ም የቀረብኩ ሲሆን ስለኑዛዜ ምንም አልተነገረም፤ በአመቱ መጥሪያ ደርሶኝ ስቀርብ ዳኛው ኑዛዜውን በተመለከተ እንዲሻር የምትፈልጉ ክስ ማቅረብ ትችላላችሁ ሲሉ ኑዛዜ መኖሩን አውቄአለሁ፤ አባቴ በኑዛዜው ላይ ካለው ግማሽ መኖሪያ ቤት ለእኔ ሰጥቷል የተባለው ብር 500 ብቻ ነው፤ ስለሆነም በስር ፍርድ ቤቶች የአመልካችን ክስ በይርጋ ውድቅ በማድረግ የተሰጠው ብይን መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች ኑዛዜው ሲፈስ ወይም ሲነበብ ያልነበሩ መሆኑ በፍሬነገር ደረጃ ስለተረጋገጠ ኑዛዜው መኖሩን ካወቁበት ጊዜ አንስቶ በሕጉ በተመለከተ 15 ቀን ውስጥ ኑዛዜው አይጸናም የሚሉበትን መግለጫ፤ እንዲሁም በ 3 ወር ጊዜ ውስጥ ደግሞ ኑዛዜው እንዲፈርስ አልጠየቁም በሚል የቀረበው የኑዛዜ ይፍረስልኝ ክስ በይርጋ ቀሪ ነው መባሉ በሰ.መ.ቁ 82585 ( በቅጽ 15 እንደታተመው ) 21769 እና 245055 ላይ ከተሰጡት አስገዳጅ ውሳኔዎች እና ከፍትሐብሔር ሕጉ ቁጥር 973 እና 974 አንጻር ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለው የይርጋ ጊዜን ተጠሪዎች በተገኙበት ለመመርመር ሲባል በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ቁጥር 2/4(ለ)እና(ሸ) 28(3) እና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 7(3) መሠረት ተጠሪዎች ቀርበው መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ከ1ኛ እስከ 3ኛ ያሉት ተጠሪዎች ግንቦት 30 ቀን 2015 ዓ.ም በሰጡት መልስ፡- ሟች ያደረጉት ኑዛዜ 1ኛ ተጠሪ ከአመልካች እና ከ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በተሰጣቸው የውክልና ስልጣን መሠረት በአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በማጸደቅ የኑዛዜ ወራሽ መሆናቸውን አመልካች አይክዱትም፤ አመልካች 1ኛ ተጠሪን ሲወክሉ በወኪላቸው የሚሰሩ ስራዎችን እስካላሻሩ ድረስ ስራው ጸንቶ ይቆያል፤ 4ኛ ተጠሪ የሟች አባታችን የውርስ ሀብት ሲያጣሩ ተጠሪዎች ስናመለክት የኑዛዜውን ወራሽነት ማስረጃ በመያዝ ጣልቃ ለመግባት ስናመለክት አመልካች ያውቃሉ፤ 4ኛ ተጠሪ ኑዛዜውን ካላሻሩ በቀር የውርስ ማጣራት ስራው እንደማይቀጥል ሲነገራቸው ኑዛዜውን የማያውቁ በመምሰል ቀርበዋል፤ ስለሆነም ይህንኑ መሠረት በማድረግ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ስለሆነ ሊጸና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

4ኛ ተጠሪ ግንቦት 30 ቀን 2016 ዓ.ም በሰጡት መልስ፡- ኑዛዜው ሲደረግም ሆነ ኑዛዜው በምስክሮች ፊት ሲፈስ አመልካችም ሆነ 4ኛ ተጠሪ በቦታው አልነበርንም፤ አመልካች እና ተጠሪ ሟች አባታችን ከሞተ በኋላ ወዲያውኑ የወራሽነት ማስረጃችንን በፍርድ ቤት ማስወሰናችን ስለኑዛዜው እንደማናውቅ ያመለክታል፤ ከአመልካች የምለየው 4ኛ ተጠሪ ከሰራኋቸው ቤቶች በቀር በግቢው ውስጥ የተሰሩ ቤቶች የሉም፤ ስለሆነም ኑዛዜው እንዲሻር የቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ሊሆን አይገባም ተብሎ ሊወሰን ይገባል የሚል ነው፡፡

አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸውን ይመስላል፡፡ ይህ ችሎትም ያስቀርባል ሲባል የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ተጠሪዎች አመልካች ከስራው ሲመጣ በቤት ቤተሰብ ባለበት ስለኑዛዜው አሳውቀነዋል ያሉ ቢሆንም ኑዛዜው በሚፈስበት / በሚነበብበት / ወቅት አመልካች ያልነበሩ ስለመሆኑ እና ኑዛዜው መኖሩን ያወቁት በወኪላቸው አማካኝነት በቀን 11/10/2013 ዓ.ም በራሳቸው ደግሞ ከቀን 14/12/2013 ዓ.ም ጀምሮ መሆኑን

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ፍሬነገር ሲሆን አመልካች ይህ ኑዛዜ እንዲሻርላቸው ክስ ያቀረቡት ደግሞ በቀን 18/12/2014 ዓ.ም ነው፡፡ የስር የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአመልካችን ክስ በይርጋ ውድቅ ያደረገው አመልካች ኑዛዜ መኖሩን ካወቁ በኋላ በሕጉ በተቀመጠው የ 15 ቀን ጊዜ ውስጥ ኑዛዜው አይጸናም የሚሉበትን ምክንያት መግለጫ አላቀረቡም በሚል ነው፡፡

በመሠረቱ ይርጋ አንድን መብት ለማስከበር የሚቀርብ ክስ ቀሪ የሚያደርግ ነው፡፡ ከሳሽ የሆነው ወገን መብቱን ለማስከበር በሕጉ ተለይቶ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ክሱን ካላቀረበ ጊዜው ካለፈ በኋላ የሚያቀርበው ክስ በይርጋ ቀሪ ይሆናል፡፡ ይሕም የይርጋ ደንብ ከሳሽ የሆነው ወገን ክስ በሚያቀርብበት ንብረት ወይም ገንዘብ ላይ ክሱን ለማቅረብ የሚያስችል መብት ቢኖረውም በጊዜው ባለማቅረቡ ብቻ መብቱን ማስከበር የማይችልበት ሁኔታ መኖሩን ታሳቢ ያደረገ ሲሆን መሠረታዊ ዓላማውም ዳተኛ የሆነ ተከራካሪ ወገን እንዳይፈጠር ማድረግ ነው፡፡

ኑዛዜ ፈራሽ ነው የሚል ክስ የሚቀርብበትን ጊዜ አስመልክቶ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 973 እና 974 ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ በዚሁ ድንጋጌ በቁጥር 973(1)(3) ላይ ኑዛዜው ሲነበብ የነበሩ ወይም የተወከሉ ሰዎች ኑዛዜው አይጸናም ወይም አንዱ በኑዛዜው የተነገረ ቃል አይጸናም በማለት ክስ ለማቅረብ ያላቸውን ሐሳብ መግለጫ ወይም ስለ ክፍያው በሒሳብ አጣሪው የቀረበውን የድልድልን አመዳደብ አሳብ ለመቃወም ኑዛዜው ከተነበበት ቀን አንስቶ የሚቆጠር የአስራ አስምት ቀን ጊዜ እንዳላቸው፤ መግለጫው ከተሰጠበት ቀን አንስቶ እስከ ሶስት ወር ጥያቄአቸውን ለዳኞች ወይም ለሽምግልና ዳኞች ካላቀረቡ በቀር የመጠየቅ መብታቸውን እንደሚያጡ ተመልክቷል፡፡ የድንጋጌው ቁጥር 974(1)(2) ደግሞ በኑዛዜው ንባብ ሥነ ሥርዓት ላልነበሩ ወይም በኑዛዜው ንባብ ሥነ ሥርዓት በወኪልነት ላልሰሙ ሰዎችን እንዲሁም ኑዛዜው በሌሉበት ይህ የተባለው ጊዜ የሚቆጠርበት መነሻ አጣሪው ስለ ክፍያው የድልድል አመዳደብ አሳቡን ከነገራቸው ቀን አንስቶ እንደሆነ፤ ኑዛዜው ከፈሰሰበት ጊዜ ከአምስት ዓመት በኋላ ወይም ኑዛዜ የሌለ እንደሆነ ሟቹ ከሞተ ከአምስት ዓመት በኋላ ስለኑዛዜው መጽናትን ስለ ክፍያው አመዳደብ አጣሪው ያቀረበው የድልድል አሳብ በማናቸውም አስተያየት  ቢሆን መቃወሚያ ሊቀርብበት አይችልም በማለት በግልጽ ተመልክቷል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 82585 ( በቅጽ 15 ላይ እንደታተመው )፤ 244047  እና በሌሎችም መዛግብት በሰጠው ውሳኔም የፍ/ብ/ሕ/ቁ  973 እና 974 ድንጋጌዎች አቤቱታ አቅራቢው ኑዛዜው ሲነበብ የነበረ ወይም የተወከለ የመሆን አለመሆኑን መስፈርት መሰረት በማድረግ ይርጋው መቆጠር የሚጀምርበትን ጊዜ እና ፍጹም የሆነ የይርጋ ጊዜ በተለየ ሁኔታ ከመደንገጋቸው በስተቀር ሁለቱም ድንጋጌዎች ኑዛዜው ፈራሽ ነው የሚል ክስ የሚቀርብበትን ስርዓት የሚደነግጉ በመሆናቸዉ ተያይዥነት እንዳላቸው፤ በፍ/ሕ/ቁ 973/1 ላይ የተመለከተው የ15 ቀን የጊዜ ገደብ የክስ ማቅረቢያ ጊዜ ሳይሆን የመግለጫ ማቅረቢያ ጊዜ እንደሆነ፤ የንብረት ድልድሉን እንዲያውቅ ያልተደረገው

ወገን መግለጫ የማቅረብ ግዴታ እንደሌለበት፤ የዚህ ዓይነቱ ግዴታ ከሌለ ደግሞ ጊዜው መቆጠር የሚጀምረው በኑዛዜው የተደረገውን የንብረት ድልድል መታወቁ ከተገለጸበት ጊዜ ጀምሮ እንደሆነ በመግለጽ በየትኛውም እርከን ላይ ለሚገኙ ፍርድ ቤቶች አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች ኑዛዜው ሲፈስ ያልነበሩ በመሆኑ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለው የይርጋ ድንጋጌ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 974 የተመለከተው የአምስት ዓመት የይርጋ ጊዜ ነው፡፡ አመልካች ኑዛዜ መኖሩን ያወቁት በወኪላቸው አማካኝነት በቀን 11/10/2013 ዓ.ም በራሳቸው ደግሞ ከቀን 14/12/2013 ዓ.ም ጀምሮ በመሆኑ የይርጋ ጊዜው መቆጠር ያለበት ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት አመልካች ኑዛዜ መኖሩን ካወቁበት ጊዜ ጀምሮ ክስ እስካቀረቡበት ቀን 14/02/2015 ዓ.ም ድረስ ያለው ጊዜ ሲቆጠር በሕጉ የተመለከተው የ5 ዓመት ጊዜ አላለፈም፡፡ ስለሆነም ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት አመልካች የኑዛዜውን መኖር ካወቁ በኂላ በሕጉ በተቀመጠው 15 ቀን ውስጥ ኑዛዜው አይጸናም የሚሉበትን ምክንያት መግለጫ ያላቀረቡ በመሆኑ ጥያቄያቸው በይርጋ ቀሪ ነው በማለት የአመልካችን ክስ በብይን ውድቅ ማድረጉ፤ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንኑ ብይን ማጽናቱ ቀደም ሲል በተመሳሳይ ጉዳይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠውን የሕግ ትርጉም ያላገናዘበ እና መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 183116 የካቲት 28 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ብይን፤ ይህንኑ ብይን በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 306516 የሰጠው ብይን ተሽሯል፡፡
2. ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት አመልካቾች ሚች አቶ ታደሰ ታዬ ያደረጉት ኑዛዜ እንዲፈርስ ያቀረቡት ክስ በይርጋ አይታገድም በማለት ወስነናል፡፡
3. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በብይን የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ የአመልካቾች ክስ በይርጋ ይታገዳል በማለት የሰጠው ብይን በዚህ ችሎት የተሻረ መሆኑን አውቆ በፍሬነገሩ ላይ ግራቀኙን አከራክሮ ተገቢ ነው ያለውን ሕጋዊ ውሳኔ እንዲሰጥበት በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341 መሠረት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
4. በዚህ መዝገብ ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፤
   - መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

መ/ዐ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት**

የመ/ቁ/252723

ጥቅምት 08/2017 ዓ.ም

**ዳኞች፡ እትመት አሰፋ**

**ደጀኔ አያንሳ**

**ኑረዲን ከድር**

**መላኩ ካሳዬ**

**ሀብታሙ እርቅይሁን**

**አመልካቾች፡**
1. **ወ/ሮ መቅደስ ጌታቸው**
2. **ወ/ሮ ይህችዓለም ጌታቸው**
3. **አቶ ገብሩ ጌታቸው**
4. **ወ/ሪት ማስተዋል ጌታቸው**

} **ጠ ሄለን ያለው ቀረቡ**

**ተጠሪዎች፡**
1. **ወ/ሮ ሀረግዋ ቢተው፤**
   **በእራሳቸው እና ሞግዚት በሆንዋት ተማሪ መክሊት ጌታቸው ስም**
2. **ወጣት ሁሉባንተ ጌታቸው አልተጠሩም**
3. **ወ/ሪት ኤልሳቤጥ ጌታቸው አልቀረቡም**

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍርድ**

በመዝገቡ ላይ የቀረበው ጉዳይ ከውርስ ሀብት ማጣራት ጋር ተያይዞ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/297397 ላይ ግንቦት 30/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት የቀረበውም ክርክር

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የቀረበበት የኮንዶሚኒየም ቤት የአመልካቾች ወላጅ አባት በውርስ ያገኙት ይዞታ በልማት በመወሰዱ ምክንያት በምትክነት ለአመልካቾች አባት የተሰጣቸው ስለመሆኑ የውርስ አጣሪው ማጣራቱን ገልፆ እያለ ቤቱ የባልና ሚስት የጋራ ሀብት ነው በሚል የተወሰነበት አግባብ ይኸው ችሎት በመ/ቁ/ 237381 ላይ ከሰጠው የህግ ትርጉም አንፃር መርምሮ ለመወሰን ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው የአሁን አመልካቾች የሟች አባታቸው አቶ ጌታታቸው ደጉን ውርስ አጣርተው ለማቅረብ እንድፈቀድላቸው ጥር 03/2014 ዓ.ም ጽፈው ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረቡት አቤቱታ ነው፡፡ በዚሁ ሂደትም የአሁን ተጠሪዎች 1ኛ ተጠሪ የሟቹ ሚስት፣ የተቀሩት ደግሞ የሟቹ ልጆች መሆናቸውን ጠቅሰው የውርስ ማጣራት ሂደቱ እነርሱን ባማከለ መልኩ እንዲከናወን ጠይቀዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙ በተሳተፉበት የሟች የውርስ ሀብት ተጣርቶ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቶ ሚያዝያ 12/2014 ዓ.ም የተዘጋጀ የውርስ አጣሪ ሪፖርት ቀርቧል፡፡ በሪፖርቱ ላይም ግራ ቀኙ ያላቸውን ሀሳብ እንዲያቀርቡ አድርጓል፡፡ በግራ ቀኙ ክርክር ከቀረበባቸው ንብረቶች ውስጥ አንዱ ከላይ የተመለከተው ኮንዶሚኒየም ቤት ነው፡፡ በዚሁ ነጥብ ላይ የቀረበውን ክርክር እና ማስረጃን ከሰማ በኋላ በሰጠው ውሳኔ ክርክር የቀረበበት ቤት ለአሁን አመልካቾች ወላጅ አባት የተሰጠው የልማት ተነሺ አርሶ አደር ልጅ ናቸው በሚል ምክንያት እንደሆነ፣ ለቤቱ መገኘት ምክንያት የሆነው ይዞታ ከአመልካቾች አባት ወላጆች ላይ ሲወሰድ በወቅቱ በነበረው መንግስት ወይም የፖሊቲካ ድርጅት ተገቢ ነው የተባለው ካሳ ተከፍሏቸው እንደነበር ግምት የሚወሰድበት መሆኑን፣ ይህ ከሆነ በኋለ አሁን ላይ የተሰጠው ካሳ በቂ አይደለም በሚል በሌላው የሀገሪቱ ክፍል ከተፈፀመው ተመሳሳይ ድርጊት በተለየ መልኩ በአዲስ አበባ ዙሪያ የሚገኙ አርሶ አደሮች በልማት ምክንያት ተጎጂ ሆነዋል በሚል ፖሊቲካዊ ውሳኔ በጋራ መኖሪያ ቤት ተመዝጋቢዎች የቁጠባ ገንዘብ የተሰራን ኮንዶሚኒየም ቤት ለአርሶ አደር ልጆች የታደላቸው መሆኑን፣ የአመልካቾች አባትም በዚሁ አኳኋን ክርክር የተነሳበትን ቤት የወሰዱ ሲሆን ቤቱ በጋብቻ ውስጥ የተገኘ በመሆኑ የግል የሚባልበት አግባብ የለም በማለት ቤቱ የሟች እና 1ኛ ተጠሪ የጋራ ንብረት ሆኖ የውርስ ሀብት የሚሆነው ግማሹ ብቻ ነው በሚል ከዚሁ አኳያ የውርስ አጣሪ ሪፖርቱን አሻሽሎ አጽድቋል፡፡

አመልካቾች ይህንኑ የውሳኔ ክፍል እንዲሁም የኪራይ ገንዘብን አስምልክቶ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ የኪራይ ገንዘቡን አስምልክቶ በቀረበው ቅሬታ ላይ ብቻ ይግባኙን በማስረቀብ አከራክሮ በነጥብ ለስር ፍርድ ቤት መልሷል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የኮንዶሚኒየም ቤቱ የተጋቢዎች የጋራ ሀብት ነው በሚል የተሰጠው የውስኔ ክፍል በመቃወም ያቀረቡት የይግባኝ አቤቱታ ተቀባይነት ማጣቱን በመቃወም

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ነው፡፡ አመልካቾች ነሐሴ 25/2015 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ ከላይ በዚህ ፍርድ መግቢያ ላይ የተጠቀሰውን ነጥብ አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል ተብሎ ግራ ቀኙ በጽሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና መሰረታዊ የክርክሩ ይዘት ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፣ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡

በቅድሚያ ግን በቀዳሚው ፍርድ ቤት ጉዳዩን ያዩት ዳኛ ለውሳኔያቸው በመንደርደሪያነት የተጠቀሙትን ምክንያት እና የአገላለጹን አግባብነት ከመሰረታዊ የፍርድ አጻጻፍ ሥርዓት አኳያ አንድ ነገር ማለቱ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ እንግዲህ ለዳኛ ውሳኔ መሰረቱ ህግ እና አግባብ ባለው የማስረጃ አቀባበል ሥርዓት መሰረት የተፈቀደ ማስረጃ ነው፡፡ ፍርድ/ውሳኔ አንድ ዳኛ የሚሰራበትን የዳኝነት ተቋም ወክሎ የቀረበለትን ጉዳይ ህግ እና በማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር ብቻ መሰረት አድርጎ ስለመመልከቱ ለተከራካሪ ወገኖቹም ሆነ ፍርዱን ለሚያነበ ሌላ ሰው የሚገልፅበት የፍርድ ቤቱ መግባቢያ ሰነድ ነው፡፡ ይህ በመሆኑም የፍርዱ አጻጻፍ በተቻለ መጠን በግራ ቀኙ በተነሳው ክርክር እና ከዚሁ ጋር በተያያዘ በማስረጃ በተረጋገጠው ፍሬ ነገር ላይ የሚያጠነጥን እንጂ በማናቸውም ሁኔታ ከክርክሩ አድማስ ወጥቶ የዳኛውን የግል አተያይ፣ እምነት እና አቋም የሚያንጸባርቅ እንዳይሆን ከፍ ያለ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አከራካሪ የነበረው ነጥብ ኮንዶሚኒየም ቤቱ የባልና ሚስት የጋራ ሀብት ነው ወይስ የአመልካቾች አውራሽ የግል ንብረት ነው የሚለው ነው፡፡ ከዚሁ ነጥብ ጋር ተያይዞ በማስረጃ የተረጋገጠው ፍሬ ነገር ለኮንዶሚኒየም ቤቱ መገኘት መሰረቱ ቀደም ሲል በልማት ምክንያት ከአመልካቾች አውራሽ ወላጆች ስር በመንግስት የተወሰደው ይዞታ መሆኑን፣ የአመልካቾች አውራሽም ቤቱን ያገኙ የተነሺ አርሶ አደር ልጅ ናቸው በሚል እንደሆነ ነው፡፡ ክርክሩ እና ማስረጃው ይህንን የሚጠቅስ ከሆነ ደግሞ የፍርድ ቤቱ ትችትም ሆነ አቋም ሊያተኩር የሚገባው ይኸው ፍሬ ነገር ከህግ አኳያ በሚኖረው ውጤት ላይ ነው፡፡ ሆኖም ከላይ ቀንጨብ ተደርጎ ከሰፈረው የስር ፍርድ ቤቱ የፍርድ ሀተታ መገንዘብ እንደሚቻለው ሀሳቡ ከቀረበው ክርክር እና በማስረጃ ከተረጋገጠውም ፍሬ ነገር በእጅጉ ያፈነገጠ ነው፡፡ የተጠቀሰው ምክንያትም ሆነ ምክንያቱ የተገለፀበት አኳኋን ሲታይም በህግ እና በማስረጃ ላይ የተሰጠ ዳኝነታዊ ትችት ሳይሆን የግል አተያይን እንደ ፍርድ ቤት ግንዛቤ/Judicial Notice/ በመውሰድ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

እርግጥ ነው የፍርድ ቤት ግንዛቤ አንድ የፍሬ ነገር ማረጋገጫ ነው፡፡ ሆኖም ፍርድ ቤት በዚህ መልኩ ግንዛቤ የሚወስድበት ጉዳይ በማስረጃ መረጋገጥ የማያስፈልጋቸው፣ አለፍ ሲልም በማስረጃ ሊስተባበል የማይችል በጠቅላው እውነትነት ባለው ጉዳይ ላይ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ባለው ጉዳይ ላይ ግን አንድ ነገር በማስረጃነት ከመወሰዱ በፊት አግባብ ባለው የማስረጃ ስነ ስርዓት መሰረት አስፈላጊውን ፍሬ ነገር ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አንፃር ፍርድ ቤቱ በማስረጃ ሊረጋገጥ በሚገባ ጉዳይ ላይ የፍርድ ቤት ግንዛቤን መውሰዱ የተሳሳተ አረዳድን መሰረት ያደረገ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቱ ከቀረበው ክርክር እና በማስረጃ ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር ባፈነገጠ መልኩ ያሰፈረው ሀሳብ የህግም ሆነ የማስረጃ ድጋፍ የሌለው ከመሆኑ በላይ አገላለጹም ጭምር መሰረታዊ የፍርድ አፃፃፍ ስርዓትን ያልተከተለ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፡፡

ዋናውን የሙግት ነጥብ በተመለከተ ለክርክሩ ምክንያት ለሆነው ኮንዶሚኒየም ቤት መገኘቱ ከአመልካቾች አውራሽ ወላጆች ስር በልማት ምክንያት በመንግስት የተወሰደው ይዞታ መሆኑን፣ ቤቱም ቢሆንም ለአመልካቾች አውራሽ የተሰጣቸው ተጎጂ የልማት ተነሺ አርሶ አደር ልጅ ናቸው በሚል ምክንያት ስለመሆኑ የውርስ አጣሪው ለፍርድ ቤቱ ባቀረበው ሪፖርት ውስጥ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ የስር ፍርድ ቤቱም ቢሆን በሌላ ምክንያት ቤቱ የተጋቢዎቹ የጋራ ንብረት ነው በሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰ ቢሆንም ይህንኑ ፍሬ ነገር በማስረጃ ማረጋገጡን ጠቅሷል፡፡ በእርግጥ በህግ አግባብ የተመሰረተ ጋብቻ ከሚያስከትላቸው ህጋዊ ውጤቶች ውስጥ አንዱ በተጋቢዎቹ መካከል የጋራ የንብረት ባለቤትነትን (Communality of Property/ የሚያቋቁም መሆኑ ነው፡፡

በዚሁ አግባብ ተጋቢዎች ጋብቻቸውን ከፈፀሙበት ቀን ጀምሮ በጋብቻ ውስጥ የሚያፈሯቸው ንብረቶች በሙሉ የጋራ ንብረት ናቸው ተብሎ የህግ ግምት እንደሚወሰድ በተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 57 እና 62 ስር ተመልክቷል፡፡ በእነዚህ ህግጋት በንብረት ረገድ የተወሰደው ህጋዊ ግምት መነሻው ተጋቢዎች የአስተዋጽዋቸው ደረጃ የተለያየ ቢሆንም በጋብቻ ውስጥ በሚፈራው ንብረት መገኘት ላይ እንደአቅማቸው እና ገቢያቸው መጠን የየራሳቸው የዓይነትም ሆነ የአገልግሎት አበርክቶ ይኖራቸዋል በሚል ምክንያት እና ንብረቱም በዚሁ አኳኋን የተፈራ ነው ከሚል እሳቤ እንደሆነ መገንዘዘብ ይቻላል፡፡ ህጉ በዚህ መልኩ ግምት የወሰደ ቢሆንም ንብረቱ የአንደኛው ተጋቢ የግል ንብረት መሆኑን በማረጋገጥ በህግ ረገድ የተወሰደን ግምት ቀሪ ማድረግ የሚቻል ስለመሆኑ በቤተሰብ ህጉ አንቀፅ 63 ስር ተመልክቷል፡፡

እንግዲህ የንብረት ጉዳይ የኢኮኖሚ ጥቅም ጉዳይ ነው፡፡ ከአንድ ንብረት የተገኘን ወይም የሚገኝን ጥቅም ለመጋራት ደግሞ በንብረቱ መገኘት ውስጥ የራስ አበርክቶ ሊኖር ይገባል፡፡ ከላይ ከተመለከቱት የህጉ አጠቃላይ መንፈስ መረዳት የሚቻለውም "የጋራ ባለሃብትነት" በሚለው የህግ ግምት ማዕቀፍ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ጥበቃ ማድረግ የተፈለገው በተጋቢዎች የጋራ ጥረት እና አስተዋፅዖ ለተፈራው ንብረት እንጂ "ጋብቻ" በሚለው ተቋም ሽፋን ብቻ ለንብረቱ መፈራት አንዳችም አስተዋፅዖ ያልነበረውን ተጋቢ የማይገባውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እንዲያገኝ ማድረግ እንዳልሆነ ነው፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው የጋራ መኖሪያ ቤት የአመልካቾ አውራሽ እና 1ኛ ተጠሪ በጋብቻ በነበሩበት ወቅት የተገኘ ቢሆንም የመብቱ ምንጭ የአሁን አመልካቾች አውራሽ የልማት ተነሺ አርሶ አደር ልጅነት ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ተጠሪዎችም ቢሆኑ ቤቱ በትዳር ቆይታ ወቅት የተገኘ በመሆኑ የጋራ ንብረት ሊባል ይገባል በማለት ከሚከራከሩ በቀር 1ኛ ተጠሪም የተነሺ የልማት ተፈናቃይ አርሶ አደር ልጅ ሆነው ቤቱ በሚች ባለቤታቸው በኩል ብቻ እንዲገኝ የተደረገ ስለመሆኑ የቀረበ ክርክርም ሆነ የተረጋገጠ ነገር የለም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ በአመልካቾች አውራሽ ወላጆች ላይ ከትዳር በፊት በልማት ምክንያት በደረሰባቸው ጉዳት መነሻነት በትዳር ውስጥ ለአውራሽ አባታቸው በካሳ መልክ የተሰጠው ቤት የተጋቢዎች የጋራ ንብረት የሚሆንበት የህግ አግባብ የለም፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘም ይኸው ችሎት በመ/ቁ/237381 ላይ ጥቅምት 30/2016 ዓ.ም በዋለው ችሎት በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ በሰጠው የህግ ትርጉም ከትዳር በፊት በልማት ተነሺነት ምክንያት በደረሰ ጉዳት መነሻነት በትዳር ውስጥ ለአንደኛው ተጋቢ በካሳ መልክ በመንግስት የተሰጠ የጋራ መኖሪያ ቤት የጋራ እንዲሆን በተጋቢዎች የተደረገ ስምምነት ከሌለ አልያም በትዳር ውስጥ ቤቱን የጋራ ሊያደርግ የሚያስችል መሻሻል የተደረገበት ስለመሆኑ ካልተረጋገጠ በቀር የተጋቢዎች የጋራ ንብረት ሊባል አይችልም በሚል ወስኗል፡፡ ከዚህ ችሎት የሚሰጥ የህግ ትርጉም ደግሞ ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በማናቸውም እርከን ላይ በሚገኝ የፌዴራል ሆነ የክልል ፍርድ ቤት ላይ የአስገዳጅነት ኃይል ያለው ስለመሆኑ በፌዴራል ፍርድ ቤቶ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 10 ስር ተደንግጓል፡፡

ጉዳዩ ይህ ሆኖ እያለ ቀዳሚ ፍርድ ቤቱ በማስረጃ ያልተደገፈ አግባብነትየሌላቸውን ምክንያቶች ጠቅሶ ቤቱ የአመልካቾች አውራሽ እና 1ኛ ተጠሪ የጋራ ንብረት ነው ማለቱ እና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ይህንኑ ሳያርም ማለፉ ለንብረቱ መገኘት መሰረት የሆነውን መብት ባህሪ ያላገናዘበ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ በአብላጫ ድምጽ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ውሳኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/179496 ላይ ህዳር 20/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ወረዳ 09 ክልል ውስጥ የካርታ ቁጥር

አቃ/ቃ/09/0018533/00 የሆነው ኮንዶሚኒየም ቤት የአመልካቾች አውራሽ እና የ1ኛ ተጠሪ የጋራ ንብረት ነው በሚል የውርስ አጣሪ ሪፖርትን በማሻሻል የሰጠው የውሳኔ ክፍል እና ይህንን በውጤት ደረጃ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/297397 ላይ ግንቦት 30/2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) እና የሰበር ስነ ስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9/1/ለ// መሰረት ተሽረዋል፡፡

2. ከላይ በውሳኔ ተራ ቁጥር 1 ስር የተጠቀሰው የጋራ መኖሪያ ቤት/የኮንዶሚኒየም/ ሟች አቶ ጌታቸው ደጉ የልማት ተነሺ የአርሶ አደር ልጅ በመሆናቸው ምክንያት ያገኙት በመሆኑ እና ቤቱን የጋራ ሊያደርግ የሚችል በትዳር ወቅት የተደረገ መሻሻል አልያም ከዚሁ አንፃር በሟቹ እና 1ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገ ስምምነት ባለመኖሩ የሟች አቶ ጌታቸው ደጉ የግል ሀብት ነው ተብሏል፡፡

## ትእዛዝ

1. የዚህን ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ ካለ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ/ጋ

## የሃሳብ ልዩነት

ስሜ በተራ ቁጥር አምስት ላይ የተሰየምኩት ዳኛ ከአብላጫው ሃሳብ የተለየሁበትን ምክንያት እንደሚከተለው አስፍሬያለሁ፡፡

ከክርክሩ እንደተገነዘብኩት በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለከተማ ወረዳ 9 በካርታ ቁጥር ቃ/ቀ/09/001853/00 የሆነ የጋራ መኖሪያ ኮንዶሚኒየም ቤት የተፈራው ወይም የተገኘው የአመልካቾች አውራሽ አቶ ጌታቸው ደጉና 1ኛ ተጠሪ በትዳር ግንኙነነት በነበሩበት ጊዜ መሆኑ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡ የገጠር መሬት ባለይዞታዎች የሟች አቶ ጌታቸው ወላጆች ሲሆን መሬቱ በልማት በመወሰዱ ምክንያት ምትክ ንብረት ወይም ካሣ ይሰጣቸዋል፤ ከጋብቻ በፊት የነበረ ንብረት በልማት ተወስዶ የሚሰጥ ምትክ ወይም ካሳ የግል ሀብት ሆኖ ይቀጥላል፡፡ ሟች አቶ ጌታቸው ደጉ ወላጆቻቸው

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

እንጂ እርሳቸው የገጠር መሬቱ ባለይዞታ ባለመሆናቸው ንብረቱ በምትክነት ወይም በካሣ የተገኘ አይደለም፤ ቤቱ የተገኘው የአመልካቾች  አውራሽ የአርሶአደር ልጅ በመሆናቸው ምክንያት በአዲስ አበባ ግብርና ልማት ኮሚሽን በወጣ መመሪያ ቁጥር 003/2001 መሠረት ነው። ይሕም የንብረት መብቱ ምንጭ ሕግ ሆኖ ከምትክና ካሣ የተለየ የሕግ ማዕቀፍ መሆኑን ያሳያል፤ የአመልካቾች አውራሽ ከሕግ ሆነ ከውል በመነጨ ሁኔታ በትዳር ላይ እያሉ ንብረት ካፈሩ ወይም የንብረት ባለመብት ከሆኑ ንብረቱ የጋራ ወይስ የግል ንብረት ይሆናል የሚለው ጉዳይ የሚወሰነው እና የሚገዛው በቤተሰብ ሕግ እንጂ በግብርና ልማት ኮሚሽን በወጣ መመሪያ መሠረት አይደለም። መመሪያው ስለባልና ሚስት ንብረት ውጤት የማይደነግግ ከመሆኑም በላይ ስለባልና ሚስት የንብረት ውጤት ቢደንግግ እንኳን የቤተሰብ ሕግ የሆነውን አዋጅ ቁጥር 213/1992 ተቃርኖ ውጤት ሊኖረው አይችልም።

በፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 62/2 መሠረት ባልናሚስት ከተጋቡ በኋላ ያፈሯቸው ንብረቶች በሙሉ የጋራ ሀብት እንደሚሆኑ ተመልክቷል። ክርክር ያስነሳው ንብረት የተፈራው የአመልካቾች አውራሽ እና 1ኛ ተጠሪ ከተጋቡ በኋላ በመሆኑ ንብረቱ የጋራ ንብረት ነው። በቤተሰብ ሕጉ አንቀጾ 57 እና 58 መሠረት የግል ንብረት የሚሆነው ከጋብቻ በፊት የተፈራ ንብረት፣ ከጋብቻ በኋላ አንደኛው ተጋቢ በውርስ ወይም በስጦታ ያገኘው ንብረት እና የግል ንብረት የሆነው ሲለወጥ /ለውጡም በፍርድ ቤት ሲጸድቅ/ ስለመሆኑ በዝርዝር ተመልክቷል። ከዚህ ማዕቀፍ ውጭ በጋብቻ የተፈራ ንብረት የግል የሚሆንበት አግባብ በቤተሰብ ሕጉ የሌለ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለከተማ ወረዳ 9 በካርታ ቁጥር ቃ/ቀ/09/001853/00 የሆነ የጋራ መኖሪያ ኮንዶሚኒየም ቤት የአመልካቾችና የ1ኛ ተጠሪ የጋራ ንብረት በማለት የውርስ አጣሪ ሪፖርትን በማሻሻል የሰጡት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም በማለት በሀሳብ ተለይቻለሁ።

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

እ/ጋ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ፤252993

7/2/2017

ዳኞች ሺመክት አሰፋ

ገበየሁ ፈለቀ

አለማየሁ ሹናራ

ተናኜ ጥላሁን

ዘውዲቱ ታደስ

አመልካች፦ሁሴን መሃመድ ወኪል መሃመድ ገበየሁ - አልቀረቡም

ተጠሪ፦የደጎሎ ከተማ አስተዳደር ማዘጋጃ ቤት - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ፍርድ</u>**

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በአማራ ክልል በጃማ ወረዳ ፍ/ቤት ሆኖ አመልካች ከሳሽ ሲሆኑ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡አመልካች በቀን 30/10/2014 ዓም ያቀረቡት ክስ በዳጎሎ ከተማ ውስጥ በምስራቅ መንገድ፤በምእራብ አሰገድ ሙህየ፤በደቡብ መንገድ፤በሰሜን ማርቆስ ሃይሉ የሚያዋስኑት 250 ካ ሜ ቦታ ያለኝ ሲሆን በተጨማሪነት በማስፋፊያ መልክ የያዝኩት 111.43 ካሜ ይዞታ አለኝ፡፡በዚህ ይዞታ ላይ ምንም አይነት የአፈጻጸም ክስ ሳይቀርብብኝ በዋና ይዞታዬ በስተሰሜን አቅጣጫ 20 ካሜ ያህል በመግፋት በአጥሬና ዲሽ ላይ ተጠሪ ጉዳት አድርሶና አፍርሶ

ይዞታውን በመውሰዱ ቦታውን እንዲመልስ፤እንዲሁም አጥርና ዲሽ ላይ ለደረሰ ጉዳት በድምሩ ብር 2000 (ሁለት ሺ ብር) ወጪ ኪሳራ ተጨምሮ እንዲከፈል ተብሎ እንዲወሰን የቀረበ ነው፡፡

ተጠሪ በሰጠው መልስ አመልካች ካለው 250 ካሜ ይዞታ ውጪ የመንግስት ይዞታ ጨምሮ በማጠሩ እንዲያፈርስ ሲጠየቅ ፍቃደኛ ባለመሆኑ ክስ ቀርቦ በመ/ቁ፤0127393 አልፎ የያዘው 130 ካሜ ይዞታ እንዲያፈርስ በፍ/ቤት ተወስኖበታል፡፡ከዚህ ውጭ  መሃመድ አራጋው የተባለ ግለሰብ በሊዝ የገዛው ቦታ ስለሆነ ጨምሮ ያጠረውን አቶ መሃመድ አራጋው ተጠሪን ከሶ ተወስኖለት በአፈጻጸም ከህግ ውጪ የታጠረውን አጥር አፍርሰን አጥሩንና ዲሹ ከማስረከብ ውጪ ከአመልካች የወሰድነውም ሆነ ያለፍንበት ይዞታ የለም በማለት ተከራከረ፡፡ የስር ፍ/ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ ማስረጃ መርምሮ የአመልካች  ምስክሮች ከሰሜን አቅጣጫ 20 ካሜ ያህል ተጠሪ ማለፉን አላስረዱም በማለት የአመልካች ክስ ውድቅ እንዲሆን ወሰነ፡፡አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅሬታ ተሰምቷቸው ይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ እስከ አማራ ክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቶቹ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ አጽንተዋል፡፡

ይህ ፍ/ቤትም የሰበር አቤቱታውን እንደመረመረው ለክርክር ምክንያት የሆነው ይዞታ ተጠሪ ድንበር ገፍቶ ይዞዋል በሚል አመልካቹ ክስ ያቀረቡበት አቅጣጫ እና መጠን በማስረጃ ከተረጋገጠው አቅጣጫ እና መጠን የተለያየ ነው በሚል አመልካቹ እንደክሱ አላስረዳም ተብሎ ክሱ ውድቅ የመደረጉን አግባብነትና እና ተያያዥ ቅሬታ ነጥቦች አንጻር የተፈጸመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖር ለመመርመር ያስቀርባል በማለት የግራ ቀኙ መልስ እና የመልስ መልስ በማስቀረብ አከራክሮዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክር ይዘት አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም የቀረበውን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ፤በዚህ ችሎት ከተያዘው ጭብጥና እና ለጉዳዩ አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

አመልካች 20 ካሬ ሜትር ድንበር ታልፎ አጥርና ዲሽም ላይ ጉዳት ደረሰ ያሉት ከሰሜን አቅጣጫ ነው፡፡ በሰሜን አቅጣጫ ደግሞ አመልካች ከራሳቸው ድንበር አልፈው የመንግስትና ለሌላ ሰው የተመራ ቦታ በመያዛቸው በፍርድ ቤት የተፈረደባቸው መሆኑና የፈረሰው አጥርና የተነሳው ዲሽም በዚሁ አልፈው በያዙት ቦታ መሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ አመልካች አልፈው በያዙት ቦታ ያጠሩት አጥር ሲነሳ የሳቸው የሆነ ቦታ ተጨምሮ የተወሰደባቸው ስለመሆኑ በማስረጃ አላስረዱም፡፡ በምስራቅ አቅጣጫ አመልካች ድንበር ታልፎ አጥር የተነሳባቸው ስለመሆኑ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ያቀረቡት ክስ የለም፡፡እንዳውም የተከሳሽ ምስክሮች በምስራቅ አቅጣጫ አመልካች ከአጥር ውጪ የሚቀራቸው 50 ሳ.ሜ ይዞታ እንዳለ ገልጸዋል፡፡ይህ ማለት አመልካች በምስራቅ አቅጣጫ አጥራቸውን ሲያጥሩ 50ሳ.ሜ ለቀው ስለማጠራቸው የሚጠቁም ሲሆን፤ባለሙያ ያቀረበውም አመልካች ከምስራቅ አቅጣጫ 12.5ካ.ሜ ይዞታ እንደቀራቸው ነው፡፡በዚህ ቦታ ላይ ደግሞ ተጠሪ አጥር አፍርሶ ድንበር አለፈ ተብሎ ስላልተከሰሰ የክልሉ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተገቢ እና ህግን የተከተለ ሆኖ አግኝተነዋል በመሆኑም ከዚህ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

- የአ/ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 0338205 በሰኔ 12 ቀን 2015 አ.ም የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ሆኖ ስላገኘነው በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
- የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ ይቻቻሉ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁጥር 253178

ጥቅምት 07 ቀን 2017 ዓ/ም

ዳኞች፡-እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች፡- ወ/ሮ ሰብለ ሙሉጌታ አስናቀ ደምሴ ቀረበ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. ወ/ሮ ሙሉ እምቢያለው ቀረበ

2ኛ. ወ/ሮ አዲስዓለም ሙሉጌታ ቀረበ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ በዳኞች የእረፍት ጊዜ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

# ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች በ04/01/2016 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የአዳማ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 38411 በቀን 25/07/2015 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 42292 በቀን 17/08/2015 ዓ.ም በሰጠው ብይን ያፀናው ቢሆንም የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 417853 በቀን 14/10/2015 ዓ.ም ይህንን ውሳኔ በመሻር መወሰኑና ይህንን ውሳኔ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 431385 በቀን 19/11/2015

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ ማፅናቱ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለታቸው ሲሆን በስር ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ከሳሽ ሆነው 2ኛ ተጠሪ ተከሳሽ፤ 1ኛ ተጠሪ ጣልቃ ገብ ሆነው በውርስ ጉዳይ ተከራክረዋል፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤት በቀን 18/01/2014 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ የአመልካችና የ2ኛ ተጠሪ እናት ወ/ሮ አለሚቱ እምቢያለው በ2012 ዓም ከዚህ አለም በሞት የተለዩ መሆኑን ገልፀው ሟች በህይወት እያለ ያፈሩትን በአዳማ ከተማ ሀንጋቱ ቀበሌ ውስጥ የሚገኘውን በካርታ ቁጥር 1124/2010 የተመዘገበውን በ500 ካሜ ይዞታ ላይ ያረፈውን ቤት አራት ወራሾች እያሉ 2ኛ ተጠሪ ለብቻቸው ይዘው ለማካፈል ፈቃደኛ አለመሆናቸውን ገልጸው ጋብቻው የውርስ ሀብት ድርሻቸውን እንዲያካፍሏቸው ጠይቀዋል፡፡

2ኛ ተጠሪም በቀን 10/02/2014 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ ቤቱ የአክስታችን ወ/ሮ ሙሉ እምቢያለው ስለሆነ ጣልቃ ገብተው እንዲከራከሩ ይታዘዝልኝ በማለት ስላመለከቱ 1ኛ ተጠሪ ወደ ክርክሩ እንዲገቡ እና መልሳቸውን እንዲያቀርቡ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ሰጥቶ 1ኛ ተጠሪ በ14/03/2014 ዓም በተፃፈ ባቀረቡት መልስም ቤቱ በ1965 ዓም የያዝኩት የግል ንብረቴ እንጂ የአመልካች እናት ንብረት አይደለም፤የቤቱን ካርታ በ1972 በስሜ አውጥቼ ካርታው በእጄና በሀንጋቱ ቀበሌ የሚገኝ ሲሆን የአመልካች እናት ህይወታቸው እስካለፈበት ቀን ድረስ በቤቱ ውስጥ የኖሩት በኔ ፍቃድ እንጂ የቤቱ ባለቤት በመሆናቸው ባለመሆኑ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ በኋላ የአዳማ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ አከራካሪው ቤት የአመልካችና የ2ኛ ተጠሪ እናት ቤት ነው በማለት የ1ኛ ተጠሪን ክርክር ውድቅ በማድረግ ውሳኔ የሰጠ ቢሆንም ይህ ውሳኔ በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሽሮ ተጣርቶ እንዲወሰን ጉዳዩ በመመለሱ የአዳማ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ተገቢ ነው ያለውን ማጣራት በማድረግና ምስክሮችን ሰምቶ በሰጠው ውሳኔም አከራካሪው ቤት በአመልካችና 2ኛ ተጠሪ እናት ስም የሚገኝ መሆኑን፤ቤቱ በስማቸው የተመዘገበውም 1ኛ ተጠሪ ስልጣን ባለው አካል በተመዘገበ በ01/04/1972 ዓም በተደረገ የሽያጭ ውል ቤቱን ለወ/ሮ አለሚቱ እምቢያለው በሽያጭ አስተላልፈው፤ተገቢው ክፍያ ለመንግስት ተከፍሎ ለረዥም ጊዜ በስማቸው ሲገብሩበት የቆዩ መሆኑን አረጋግጠው መሆኑን ካርታውን የሰሩት ባለሙያዎች በችሎቱ ቀርበው ማስረዳታቸውን፤የሽያጭ ውሉ የቤት ቁጥር 328 በሚል ማመልከቱ የሽያጭ ውሉ አከራካሪውን ቤት የሚያመለክት መሆኑን እንደሚያሳይ፤ስፋት 97 ካሜ የሚለውም ቤቱ ያረፈበትን የሚያሳይ መሆኑን በመጥቀስ 1ኛ ተጠሪ በቤቱ ላይ መብት የላቸውም፤ቤቱ የውርስ ሀብት ስለሆነ 2ኛ ተጠሪ የቤቱን 1/4ኛ ድርሻ ለአመልካች ሊያካፍሉ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ይህ ውሳኔ ጉዳዩን በይግባኝ በተመለከተው የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፀንቷል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

1ኛ ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው የይግባኝ አቤቱታቸውን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው፤ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ በሰጠው ውሳኔም የአመልካችና የተጠሪዎች 1ኛ እና 4ኛ ምስክሮች ቤቱ የ1ኛ ተጠሪ መሆኑን ሲያስረዱ የአመልካች ምስክሮች የአመልካች እናት በቤቱ ውስጥ መኖሯን እንጂ የባለቤትነት መብት ያላት መሆኑን አለማስረዳታቸውን፤የሽያጭ ውሉ መዝገቡ ውስጥ የሌለና ስለውሉም በግራ ቀኙ ያልተገለፀና ውሉም 97 ካሜ ሽያጭን የሚመለከት ሆኖ ግራ ቀኙ የሚከራከሩት 500 ካሜ ላይ ስላረፈ ቤት መሆኑን፤በፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ መሰረት ተጣርቶ የቀረበው ሪፖርት ውሉ ክርክር ያስነሳውን ቦታ የማይገልፅ መሆኑን፤የ1ኛ ተጠሪ ካርታ የተሰረዘበት ምክንያት ያልተመለከተ መሆኑን፤የአዳማ ከተማ መሬት ፅ/ቤት ለስር የወረዳው ፍርድ ቤት በ25/05/2015 ዓም የፃፈው ደብዳቤ ካርታው በሟች ስም የተሰራው ትክክለኛው ሂደት ተከትሎ አለመሆኑን የሚያሳይ መሆኑን፤ሟች በቤቱ መኖሯ እና አልፎ አልፎ በስሟ መገበሯ ባለቤትነቷን የሚያሳይ አለመሆኑን በመጥቀስ ካርታን መሰረዝ የፍርድ ቤቱ ስልጣን ባይሆንም ቤቱ ግን የ1ኛ ተጠሪ መሆኑ ስለተረጋገጠ 2ኛ ተጠሪ ለአመልካች የቤቱን 1/4ኛ ድርሻ ልታስረክባት ይገባል በማለት የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ አግባብነት የለውም በማለት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡ይህ ውሳኔ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ፀንቷል፡፡

አመልካችም የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት በ04/01/2016 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ለዚህ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፦ ለክርክር መነሻ የሆነዉ መኖሪያ ቤት በቀድሞው ናዝሬት ከተማ ከፍተኛ 3፤ ቀበሌ 14 በአሁኑ አዳማ ከተማ ሀንጋቱ ቀበሌ ዉስጥ በካርታ ቁጥር 1124/72 በመለያ/የቤት ቁጥር 328 ተለይቶ የሚታወቅ በ1/4/1972 ዓ.ም በ1ኛ ተጠሪና በአመልካች እናት በወ/ሮ አለሚቱ እምቢያለዉ መካከል በተፈረመና በቀድሞው የናዝሬት ከተማ ማዘጋጃ ቤት ፊት ቀርቦ በዉል ሰነድ ቁጥር 13ኛ፤ በዉል መዝገብ 662ኛ ገጽ ላይ የቴምብር ቀረጥ ተከፍሎበት በተመዘገበ የሽያጭ ዉል መሰረት በብር 8,670.00 (ስምንት ሺህ ስድስት መቶ ሰባ ብር) ለወ/ሮ አለሚቱ እምቢያለዉ የተሸጠ ስለመሆኑ በጽሁፍ ማስረጃ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ ይህ ስለመሆኑም አልተካደም፡፡ እዉነታ ይህ ሆኖ ሳለ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የምስራት ቋሚ ምድብ ችሎት የህግ ድጋፍ የሌላዉን ምክንያት በመምዘዝ የሥር ፍ/ቤቶችን ዉሳኔ መሻሩ አግባብ አይደለም፤ለክርክር መነሻ የሆነዉ መኖሪያ ቤት ህጋዊ አሰራርን ተከትሎ አግባብ ባለዉ ባለሥልጣን ፊት ቀርቦ በጸደቀ የሽያጭ ዉል መሰረት ለአመልካች እናት ለወ/ሮ አለሚቱ እምቢያለዉ ተሽጧል፡፡ ይህን የሽያጭ ዉል ተከትሎም ገዢ ከ1972 ዓ.ም ጀምሮ በስማቸዉ ለ42 ተከታታይ ዓመታት በቤቱ ግብር ሲገብሩ ቆይተዋል፡፡

በቤቱ የግል ማህደር ዉስጥ የሚገኝ የሽያጭ ዉል እና የግብር ካርኒዎችን እንዲሁም ሌሎች ማስረጃዎችን መነሻ በማድረግ አግባብ ያለዉ ባለስልጣን ለሟች ወ/ሮ አለሚቱ እምቢያለዉ በካርታ ቁጥር 1124/72 የተለየ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በ22/06/2010 ዓ.ም ሰጥቷል፡፡ የህግ ስርዓቱና አስተዳደራዊ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አሰራሩ በሚፈቅደዉ መንገድ የተሰጠ የንብረት ባለቤትነት ማስረጃ ስለመሆኑም በወረዳ ፍ/ቤት ደረጃ በተደረገ ማጣራት ተረጋግጧል። ይህ ሆኖ እያለ የሽያጭ ዉሉ ሳይፈርስ በዉርስ ሀብት ክፍፍል ክርክር ላይ ሥልጣን ባለዉ አካል የተሰጠ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ማምከን ህገወጥ ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ዉሳኔ በፍትሐብሄር ህግ አንቀጽ 1195 ስር የተደነገገን የህግ ግምት ያልተከተለ መሰረታዊ የክርክር አመራርን የጣሰ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፤ በ01/4/1972 ዓ.ም በ1ኛ ተጠሪና በአመልካች እናት በወ/ሮ አለሚቱ አምቢያለዉ መካከል በተፈረመ የሽያጭ ዉል መስረት የተገለጸዉ ቤቱ ያረፈበት በሚል 97 ካሜ (የቤቱ ስፋት) የሚል ሆኖ ሳለ የስር ፍርድ ቤት የቤቱን ወለል ከቤቱ ይዞታ ስፋት ጋር በማደበላለቅ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ መሻሩ አግባብ ባለመሆኑ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የምስራቅ ቋሚ ምድብ ችሎት የሰጡት ውሳኔ ተሽሮ የስር የአዳማ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት እና የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ዉሳኔ እንዲፀና ይወስንልኝየሚል ነው።

አቤቱታው የቀረበለት የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ለዚህ ችሎት ከመራው በኋላ ይህ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ፦ በግራ ቀኙ ከቀረበው ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች በማስረጃ ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር አንፃር የክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በመሻ ቤቱ የ1ኛ ተጠሪ ንብረት ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ በማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር መሰረት ያደረገ እና በተገቢው ምክንያት የታገዘ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ተጠሪዎች መልስ ይስጡበት በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል።

1ኛ ተጠሪም በዚህ ትዕዛዝ መሰረት በ01/11/2016 ዓ.ም የተጻፈ መልስ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፦ ክርክር ያስነሳው ቤት በአዳማ ከተማ ቀበሌ 14 ውስጥ በካርታ ቁጥር 1124/72 ስፋቱ 500 ካሬ ሜትር ሆኖ ተመዝግቦ እንደነበረ በአመልካች የታመነ መሠረታዊ ጭብጥ ነው። ይህ ቤትም እስከ 2010 ዓ.ም ድረስ በ1ኛ ተጠሪ ስም ተመዝግቦ ይገኝ የነበረ ሲሆን በ1972 ዓ.ም በተደረገው ውል ሚች እናታችን ገዝታለች በማለት አመልካች ያቀረበችውን አስመልክቶ ተጠሪ ውሉን የማላውቀው ሲሆን ለክርክር መሠረት የሆነውንም ቤት አልሸጥኩም፤ አመልካች በካርታ ቁጥር 1124/72 የተመዘገበና በ500 ካ.ሜ ቦታ ላይ ያረፈውን ቤት አስመልክቶ አንዳችም ያቀረበችው ውልም ሆነ ማስረጃ የሌለ እና እኔም የተዋዋልኩት ውልም የሌለ በመሆኑ የአመልካች እናት ገዝታለች ያሉትም 97 ካሬ.ሜትር ቦታን የሚያመላክት በመሆኑ እና ይህም ደግሞ በይዞታ ስፋትም ሆነ በማንኛውም ነገር የተለያየ መሆኑን የሚያስረዳ በመሆኑ 97 ካሬ ሜትርንም ሆነ የ500 ካሬ ሜትር የተመለከተ ውል በመካከላችን የሌለ በመሆኑ፤መዝገቡ በተመለሰበት ወቅት እንዲጣራ ከታዘዘው አንፃር ኮሚቴው በደብዳቤ ቁጥር WLMA/01/798 በቀን04/02/2015 ለስር ፍ/ቤት በፃፈው ደብዳቤ የስም ዝውውሩ ሂደት ትክክል አለመሆኑን፤ በ1ኛዋ ተጠሪ ስም ያለው ካርታ መሰረዙ አግባብነት የሌለው መሆኑን፣ በ1972 የተደረገው የሽያጭ ውል፣ ክርክር ካስነሳው ይዞታ ጋር የሚያገናኝ አንዳችም ነገር በመሬቱ ስፋት ጭምር የሌለ መሆኑን እንዲሁም የ1ኛዋ ተጠሪ ካርታም ከመሰረዝ ውጪ ሌላ ምንም ዓይነት ሰነድ በፋይላቸው ውስጥ አለመኖሩን የስም ዝውውሩን አስመልክቶ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የሚያስፈልጉ ፎርማሊቲዎች ግዴታ እንደሆነ ተገልፆ የስም ዝውውሩ አግባብነት የሌለው መሆኑን የተገለፀ መሆኑን በማገናዘብ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ማስረጃውን በመመዘን የወረዳውን ፍ/ቤት ውሳኔ መሻሩ የሚነቀፍ አይደለም፡፡

አመልካች ክላይ በተገለፀው መሠረት በሥር ፍ/ቤት ውል የተደረገው በ97 ካ.ሜ ላይ ብቻ ነው እያሉ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ደግሞ ቤቱ ያረፈበት የወለል ስፋት ነው በማለት አዲስ ክርክር በማቅረብ የጠየቁት ዳኝነት በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 329 አግባብ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ስም የተዛወረበትን አግባብ በማጣራት መወሰናቸው በሰ/መ/ቁ.75414 ፤በሰ/መ/ቁ.99071 ቅጽ 18 እና በሌሎች መዝገቦች ላይ የተሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሰረት ያደረገ በመሆኑ ፤በወረዳ ፍ/ቤት የቀረቡት የስው ምስክሮችም ቤቱ የ1ኛ ተጠሪ መሆኑን የአመልካች እናት የ1ኛዋ ተጠሪ እህት በመሆኗ እንድትኖርበት ስለመፍቀድዋ እና ለብዙ ዓመታት ልጆቿን ይዛ ትኖርበት የነበረች እና እዛው ቤት ውስጥ ስለመሞቷ ማስረዳታቸውን በማመዛዘን ሟች ከአመልካች ውጪ 3 ልጆች ያሏት ሲሆን የአሁኗ 2ኛ ተጠሪን ጨምሮ ይህ ንብረት የእኔ የ1ኛ ተጠሪ ሀቅ እና የላቤ ውጤት መሆኑን አምነው አለመጠየቃቸው ራሱ ይህ ንብረት የኔ የ1ኛዋ ተጠሪ ንብረት ነው እንጂ አመልካቿ እንደምትለው የሟች ንብረት አለመሆኑን ስለሚያሳይ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ተደርጎ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት እና ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡትን ውሳኔ ሊፀና ይገባል የሚል ነው፡፡

2ኛ ተጠሪም በ01/11/2016 ዓ.ም የተጻፈ መልስ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፡-አከራካሪው ቤት የ1ኛ ተጠሪ የግል ንብረት ነው እንጂ የሟች እናታችን ንብረት ስላልሆነ እኔም ሆንኩ አመልካች አዚህ ቤት ላይ አንዳችም መብት ስለሌለን ቤቱን 1ኛ ተጠሪዋ ሠርታ ካርታ አወጥታበት ሳለ ሟች እናታችን ወ/ሮ አለሚቱ እምቢያለው ወኪሏ በሆነው በአመልካች ባል አቶ አስናቀ ደምሴ አማካኝነት 1ኛዋ ተጠሪ አክስታችን በፍጹም በማታውቀው መንገድ የዚህ መኖሪያ ቤት ካርታ በ2010 ዓ.ም ውስጥ ከአክስታችን ወደ እና እናታችን የተዛወረ ሲሆን በህገ ወጥ መንገድ ይህ የአክስታችን ንብረት መውረስ ስለሌለብን፤በታህሣሥ 01/1972 ዓ.ም የተደረገ እና የቦታ ስፋቱ 97 ካሬ ሜትር የተባለውን ውል አስመልክቶ በዚህ ጉዳይ ላይ አመልካችም ለስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክርክር ስለሌለ እና ከዚህ የካርታ ቁጥሩ 1124/72 የሆነ እና የቦታ ስፋት 500 ካሬ ሜትር ጋር በጭራሽ ምንም አይነት ግንኙነት ስለሌለው የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ተደርጎ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት እና ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

አመልካችም በ17/11/2016 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ አቤቱታቸውን አጠናክረዋል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተነው ሲሆን እኛም ያስቀርባል ሲባል የተያዘውን ጭብጥ ከግራቀኙ ክርክር፤ በስር ፍርድ ቤት ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች እና ከተገቢው ህግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡የሕግ ግምት አከራካሪ የሆነው ጭብጥ መኖር ወይንም አለመኖርን ፍርድ ቤት ያለ ተጨማሪ ማስረጃ አምኖ እንዲቀበል በሕግ የሚገደድበት አግባብ ነው፡፡ የሕግ ግምት የሚስተባበል ወይም

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የማይስተባበል ተብሎ የሚከፈል ሲሆን  የሚስተባበል የሕግ ግምት ነፃ በሆነ ተቃራኒ ማስረጃ የሚስተባበል ወይም ውስን በሆነ ተቃራኒ ማስረጃ የሚስተባበል ሊሆን ይችላል፡፡ የፍትሐ ብሔር ሕጉ ስለሀብትነት ማስረጃ የንብረቶችን መሰረታዊ ባህሪ ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ዝርዝር ድንጋጌዎችን የያዘ  ሲሆን በዚሁ አግባብ የተቀረፀው ቁጥር 1193(1) የሚንቀሳቀሱ ግዙፍ ንብረቶችን በተመለከተ የንብረቶቹ ባለይዞታ (ባለእጅ) የሆነ ሰው ንብረቱን በስሙ እንደያዘውና የንብረቱ ባለሀብት እንደሆነ የሚገመት መሆኑን የሚደነግግ ሲሆን ይህ የህግ ግምቱ ትክክል አይደለም በሚል የሚከራከረው ሰው በሚያቀርበው ማስረጃ የሚስተባበል መሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ.1193(2) መመልከቱ ከሚንቀሳቀሱ ግዙፍ ንብረቶች ጋር በተያያዘ የሕግ ግምቱ ነፃ በሆነ ሁኔታ  በተቃራኒ ማስረጃ የሚስተባበል መሆኑን ያሳያል፡፡

የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን በተመለከተ የባለሀብትነት ምስክር ወረቀት የሚሰጠው በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1553- 1636 ያሉትን ድንጋጌዎች መሠረት አድርጎ ሲሆን በዚህ አግባብ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነትን በማወቅ በአስተዳደር አካል የተሰጠ የባለሀብትነት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው የዚህ ንብረት ባለሀብት ተደርጎ የሚገመት መሆኑን የፍ/ብ/ህ/ቁ.1195(1) የሚደነግግ ሆኖ ይህ የህግ ግምት በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1196 ሥር በተመለከተው አግባብ ካርታው የተሰጠው ከደንብ ውጪ በሆነ አሰራር ወይም ይህን ለመስጠት ስልጣን በሌለው የአስተዳደር ክፍል ወይም በማይረጋ የምስክር ወረቀት መሠረት የተሰጠ መሆኑን በማረጋገጥ ሊስተባበል የሚችል መሆኑ መመልከቱ ከፍ/ብ/ህ/ቁ.1193(2) በተለየ መልኩ በፍ/ብ/ህ/ቁ.1195 የተመለከተው የህግ ግምት በአንድ በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ በአስተዳደር አካሉ የሚሰጥ የይዞታ ማረጋገጫ ማስረጃ ጥያቄ ሊቀርብበት የማይችል ደምዳሚ ማስረጃ አለመሆኑን፤ ከዚህ ይልቅ አግባብነት ያለውን ተቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ ሊስተባበል የሚችል የሕግ ግምት መሆኑን፤ ይህም የሚፈፀመው  ውስን የሆነ ተቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ መሆኑን ያሳያል፡፡ስለሆነም በአንድ ንብረት ላይ ባለሐብትነትን አስመልክቶ ጥያቄ በቀረበ ጊዜ የአንድ ንብረት ባለሐብት በአስተዳደር አካሉ የተሰጠው የምስክር ወረቀት እና ይህን የምሰክር ወረቀት በማስተባበል የቀረበው ማስረጃ በአግባቡ ተመዝነው የንብረቱ ትክክለኛ ባለሐብት ማነው በሚለው ላይ ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባል፡፡(በሰ/መ/ቁ.223150፤222794 እና በተመሳሳይ መዝገቦች የተሰጡ አስገዳጅ የህግ ትርጉሞችንና በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በፌ/ም/መ/ቁ.022/08 እና በተመሳሳይ መዝገቦች የተሰጡትን ትርጉሞች ይመለከቷል፡፡)

አሁን በያዝነው ጉዳይ አከራካሪው በአዳማ ከተማ ሀንጋቱ ቀበሌ ውስጥ የሚገኘው ቤት በሟች ወ/ሮ አለሚቱ እምቢያለው ስም በካርታ ቁጥር 1124/2010 ተመዝግቦ በተገቢው የአስተዳደር አካል የይዞታ ማረጋገጫ የተሰጠው መሆኑ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ.1195 መሰረት የቤቱ ባለሀብት ተደርገው የሚገመቱት ሟች ወ/ሮ አለሚቱ እምቢያለው መሆናቸውን ያሳያል፡፡1ኛ ተጠሪ ቤቱ በ1965 ዓም የያዙት የግል ሀብታቸው መሆኑን፤ከሟች ወ/ሮ አለሚቱ ጋር ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል ሳይኖር ከህጉ አግባብ ውጪ ለሟች ወ/ሮ አለሚቱ በስማቸው ካርታ ተዘጋጅቶ የተሰጣቸው

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

መሆኑን፤የቤቱን ካርታ በ1972 በስቸው አውጥተው ካርታው በእጃቸና በሀንጋቱ ቀበሌ የሚገኝ መሆኑን የአመልካች እናት ህይወታቸው እስካለፈበት ቀን ድረስ በቤቱ ውስጥ የኖሩት በፍቃዳቸው እንጂ የቤቱ ባለቤት በመሆናቸው አለመሆኑን ጠቅሰው ስለተከራከሩ የስር የአዳማ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ተገቢውን ማጣራት ማድረጉን በዚህ አግባብም አከራካሪው ቤት በሟች ወ/ሮ አለሚቱ እምቢያለው ስም የሚገኝ መሆኑን፤ቤቱ በስማቸው የተመዘገበውም 1ኛ ተጠሪ ስልጣን ባለው አካል በተመዘገበ በ01/04/1972 ዓም በተደረገ የሽያጭ ውል ቤቱን ለወ/ሮ አለሚቱ እምቢያለው በሽያጭ አስተላልፈው፤ተገቢው ክፍያ ለመንግስት ተከፍሎ ለረዥም ጊዜ በስማቸው ሲገብሩበት የቆዩ መሆኑን አረጋግጠው መሆኑን ካርታውን የሰሩት ባለሙያዎች በችሎቱ ቀርበው ማስረዳታቸውን፤የሽያጭ ውሉ የቤት ቁጥር 328 በሚል ማመልከቱ የሽያጭ ውሉ አከራካሪውን ቤት የሚያመለክት መሆኑን እንደሚያሳይ፤ስፋት 97 ካሬ የሚለውም ቤቱ ያረፈበትን የሚያሳይ መሆኑን በመጥቀስ አከራካሪው ቤት የውርስ ሀብት እንጂ የ1ኛ ተጠሪ አለመሆኑን ማረጋገጡን በውሳኔው ላይ አመልክቷል።ይህም ከህግ ግምቱ ባሻገር ማስረጃን የመስማት፤የመመርመርና የመመዘን ስልጣን ባለው የስር ፍርድ ቤት ቤት የንብረቱ የባለሀብትነት መብት ህጉን ተከትሎ የተፈጠረ መሆኑን ያሳያል።

ከላይ እንደተመለከተው ይህ በፍ/ብ/ህ/ቁ.1195(1) የተመለከተው የህግ ግምት በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1196 ሥር በተመለከተው አግባብ ካርታው የተሰጠው ከደንብ ውጪ በሆነ አሰራር ወይም ይህን ለመስጠት ስልጣን በሌለው የአስተዳደር ክፍል ወይም በማይረጋ የምስክር ወረቀት መሠረት የተሰጠ መሆኑን በማረጋገጥ አግባብነት ባለው ማንኛውም ማስረጃ ሊስተባበል የሚችል ቢሆንም 1ኛ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤቶች በተደረገው ክርክር ተገቢውን ማስረጃ በማቅረብ ይህንኑ የህግ ግምት ማስተባበላቸውን የስር ፍርድ ቤት መዝገብ አያሳይም።በፍርድ ቤቶች የማጣራት ሂደት የቀረቡት ማስረጃዎች የተመረመሩበትን አግባብ ስንመረምረውም በመጀመሪያ ጉዳዩን ያየው የአዳማ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት የማጣራት ሂደቱ ሶስት ደረጃዎችን የያዘ መሆኑን ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ በሰጠው መመሪያ መሰረት በኮሚቴ ተጣርቶ በ04/02/2015 ዓም የቀረበው ሪፖርት በሟች ወ/ሮ አለሚቱ እምቢያለውና በ1ኛ ተጠሪ መካከል በ1972 ዓም የተደረገው የሽያጭ ውል ፋይሉ ውስጥ የሚገኝ ቢሆንም ስፋቱን 97 ካሬ የሚል ግልፅነት የጎደለው በመሆኑ ተገቢው ማብራሪያ እንዲሰጥበት ለአዳማ ከተማ መሬት ፅ/ቤት ትዕዛዝ ሰጥቶ አሰራርን አስመልክቶ በ25/05/2015 ዓም ማብራሪያ የቀረበ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት መዝገብ የሚያሳይ ሲሆን ይህንን ግልፅ ለማድረግም ካርታውን በመስራት ሂደት ላይ የተሳተፉትን ባለሙያ በመጥራት ባለሙያውም የሽያጭ ውሉ ማህደሩ ውስጥ ስለሚገኝና ወ/ሮ አለሚቱ ለረዥም ጊዜ በስማቸው የገበሩ መሆኑን መነሻ በማድረግ ተገቢው የመንግስት ክፍያ እንዲከፈል ካደረጉ በኋላ ካርታውን የሰሩ መሆኑን ማስረዳታቸውን በመጥቀስ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔውን ማሳረፉን መዝገቡ ያሳያል።

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለሰጠው ውሳኔ በዋነኝነት መሰረት ያደረገው በ04/02/2015 ዓም በኮሚቴ የቀረበውን ሪፖርት ሲሆን ካርታውን በመስራት ሂደቱ ላይ የተሳተፉትን ባለሙያ ዝርዝር መግለጫ ከግምት ውስጥ ያላስገባበትን ወይም ውድቅ ያደረገበትን በቂና አሳማኝ ምክንያት ያላመለከተ ሲሆን ቤቱ ከመነሻው የ1ኛ ተጠሪ መሆኑ ግራ ቀኙ ባልተካካዱበት በዚህ በታመነ ነጥብ ላይ ምስክሮቹ የሰጡትን የምስክርነት ቃል መነሻ በማድረግ ባለሙያውም ሆነ ፍርድ ቤቱ ለውሳኔው መሰረት ያደረገው ሪፖርት በ01/04/1972 ዓም በሟች ወ/ሮ አለሚቱና 1ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል በቤቱ ማህደር ውስጥ የሚገኝ መሆኑን እያስረዱ ፍርድ ቤቱ መነሻ ምክያቱን ሳያመለክት ውሉ የሌለ መሆኑን በመጥቀስ፤በማስከተልም ስለ ውሉ መኖር ግራ ቀኙ በክርክራቸው አለመግለፃቸውን በመጥቀስ በማስከተልም ውሉም ስለ 97 ካሜ እንጂ ስለአካራከሪው 500 ካሜ ቤትና ቦታ የሚገልፅ አለመሆኑን በመጥቀስ፤ከዚህ አንፃር የስር ፍርድ ቤት ውሉ የቤት ቁጥር 328 የሚል መሆኑና 97 ካሜ ግንባታ ያረፈበትን ይዞታ የሚመለከት መሆኑን በመጥቀስ ውሉ አከራካሪውን ቤትና ቦታ የሚመለከት መሆኑን በማመልከት ውሉን ተቀብሎ ለግራ ቀኙ ክርክር የሰጠበትን አግባብ ዝርዝር ምክንያት በመስጠት የሕግ ውጤት በማሳጣት ውድቅ ሳያደርግ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ መሻሩ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በክርክርና ክርክርን ለማስረዳት የቀረበን፤የተሰማን ማስረጃ አንድ በአንድ በማገናዘብ በመተቸት፤ የሚቀበለውንና የማይቀበለውን በመለየት ዳኝነት መስጠት እንደሚገባው በማመልከት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 181 እና 182 ድንጋጌዎች ስር የተመለከተውን ባላገናዘበ መልኩ ለግራ ቀኙ ክርክር እልባ በመስጠት መሰረታዊ የህግ ስህተት መፈፀሙን የሚያሳይ በመሆኑ፤ጉዳዩ የቀረበለትም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ይህንን በስር ፍርድ ቤት የተፈፀመን መሰረታዊ የህግ ስህተት ሊያርም ሲገባ ማፅናቱ አግባብነት ያለው ሆኖ ስላላገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ውሳኔ

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 417853 በቀን 14/10/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔና ይህንን ውሳኔ በማጽናት የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 431385 በቀን 19/11/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስነስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9(1)(ለ) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የአዳማ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 38411 በቀን 25/07/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔና ይህንን ውሳኔ በማፅናት የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 42292 በቀን 17/08/2015 ዓ.ም የሰጠው ብይን በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስነስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9(1)(ሀ) መሰረት ፀንቷል፡፡

3.ግራ ቀኙ በሰበር ክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

**<u>ጉዳዩ ውሳኔ ስላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡</u>**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

**ፋ/ዘ**

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የመ.ቁ.253301

ጥቅምት 07/2017 ዓ.ም

ዳኞች:እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች: ወ/ሮ መድሐኒት ተሾመ አልቀረቡም

ተጠሪ: አቶ ሙሉቀን ጥላሁን ቀርቧል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የባልና ሚስት ንብረት ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበው የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/05510 ላይ ሐምሌ 27/2015 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ ለዚህ ችሎት የቀረበውም ለግራ ቀኙ የትዳር ጥቅም ውሏል የተባለው እዳ የተጠሪ የግል ንብረት ናቸው የተባሉትን የቤት ቁሳቁሶች መግዥ ያነት የዋለ ለመሆኑ ተገልፆ እያለ አመልካች ቀሪ እዳውን እንዲከፍሉ የተወሰነበት አግባብ መርምሮ ለመወሰን ነው፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ክርክሩ የጀመረው በግራ ቀኙ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍቺ መጠናቀቁን ተከትሎ የአሁን ተጠሪ በአዋሳ አካበቢ የታቦር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት የጋራ የንብረት ክፍፍል ጥያቄ ነው፡፡ ተጠሪ ዳኝነት ከጠየቁባቸው ጉዳዮች ውስጥ ለዚህ ሰበር ክርክር ምክንያት የሆነው በጋብቻ ወቅት ከመስሪያ ቤቱ የተበደረውና ያልተከፈለው ቀሪ እዳ ብር 129,518.19 የግራ ቀኙ የጋራ እዳ ተብሎ እንዲወሰን ነው፡፡

አመልካች ለዚሁ በሰጡት መልስ ስለተባለው ብድር እንደማያውቁ እና ፍቃዳቸውንም ያልሰጡ መሆኑን ጠቅሰው የጋራ እዳ ሊባል አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃን ከሰማ በኋላ ክርክር የቀረበበት ገንዘቡ ለትዳር ጥቅም ስለመዋሉ ተጠሪ ያላስረዱ በመሆኑ የጋራ እዳ ሊባል አይገባም በማለት ውድቅ አድርጎ በተቀሩት ንብረቶች ላይም ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ቀሪ እዳው የተጠሪ የግል እዳ ነው በሚል የተሰጠው ውሳኔ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ፀንቷል፡፡

አመልካች "የተጠሪ የግል ንብረት ናቸው" በሚል በተወሰኑት ንብረቶች ላይ፤ ተጠሪ ደግሞ "እዳው የግል ነው! እንዲሁም የግል ሊባሉ ሲገባቸው የጋራ ንብረት ናቸው" በሚል በተሰጠው የውሳን ክፍል ላይ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በኩላቸውን አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ሰበር ሰሚ ችሎትም በግራ ቀኙ የቀረቡትን አቤቱታዎች አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ ሁለቱን መዝገቦች አጣምሮ በሰጠው ውሳኔ ተጠሪ "የግል ንብረቶቼ ናቸው!" በሚል የጠቀሷቸው ንብረቶች ከጋብቻ በፊት የተፈሩ በመሆናቸው የተጠሪው የግል ንብረቶች ናቸው፤ ክርክር የቀረበበት የብድር ገንዘብ በጋብቻ ውስጥ የተገኘ ሆኖ አመልካች "በብድሩ ላይ አልፈረምኩም!" ከሚሉ በስተቀር እዳው ለትዳር ጥቅም እንዳልዋለ ያላስረዱ በመሆኑ ቀሪው እዳ የጋራ እዳ ነው በማለት የሥር ፍ/ቤቶቹን ውሳኔ ከዚሁ አንፃር አሻሽሏል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች መስከረም 8 ቀን 2016 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ ተፈጽሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቋል፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ ከላይ በዚህ ፍርድ መግቢያ ላይ የተጠቀሰውን ነጥብ አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል ተብሎ ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የጉዳዩ አመጣጥ እና መሰረታዊ የክርክሩ ይዘት ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፣ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡

ከጉዳዩ አመጣጥ መገንዘብ እንደተቻለው የአሁን ተጠሪ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው በጋብቻ ውስጥ የተገኘው የብድር እዳ የጋራ እዳ ሊባል ይገባል የሚሉበት ዋነኛው ምክንያት እዳው የተገባው ጋብቻው ፀንቶ ባለበት ወቅት በመሆኑ እና ገንዘቡም ለቤት ቁሳቁስ መግዥያነት፣ የጋብቻ ሥነ ሥርዓት ማስፈፀሚያነት ውሏል በሚል ነው፡፡ አመልካች ደግሞ ለብድር ስምምነቱ ፈቃዳቸውን ካለመስጠታቸውም በላይ እዳው ስለመሆኑ ጭምር በመካድ የጋራ እዳ ሊሆን አይገባም በማለት የሚከራከሩ መሆኑን ነው፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት እዳው የጋራ ነው በሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰው አመልካች ለብድሩ ስምነታቸውን ያልሰጡ ቢሆንም ፀንቶ ባለ ጋብቻ ውስጥ የተገባ እዳ በመሆኑ እና ገንዘቡም ለትዳር ጥቅም አለመዋሉን አላስረዱም በሚል ነው፡፡

በእርግጥ ክርክሩ የተነሳበት የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የራሱ የቤተሰብ ህግ ያላወጣ ሲሆን በነባሩ ክልል የወጡ አዋጆች ተፈፃሚነት እነዲቀጥል ለመፍቀድ ባወጣው በአዋጅ ቁጥር 08/2012 መሰረት የቀድሞ ደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 75/1996 ተፈፃሚ እንዲደረገ ታውጇል፡፡ በዚህ የቤተሰብ ህግ መሰረት ከብር 500.00(አምስት መቶ) በላይ የሆነ ብድር ለማበደር ወይም ለመበደር የሁለቱም ተጋቢዎች ስምምነት የሚያስፈልግ ስለመሆኑ በአንቀጽ 77(መ) ስር ተመልክቷል፡፡ አንደኛው ተጋቢ ይህንን በመተላለፍ ያለሌላኛው ተጋቢ ከተጠቀሰው መጠን በላይ ውል ውስጥ ገብቶ የገኘ እንደሆን ስምምነቱን ያልሰጠው ተጋቢም በህጉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ውሉ እንዲፈርስ ለፍርድ ቤት ጥያቄ በማቅረብ ቀሪ ማስደረግ እንደሚችል በዚሁ ህግ በአንቀጽ 78 ስር ተመልክቷል፡፡

የዚህ ድንጋጌ መንፈስ ውሉ የአንደኛው ተጋቢ ስምምነት ሳይኖር በመደረጉ ብቻ ከጅምሩ ውጤት አልባ ነው ወደሚል ድምዳሜ የሚወስድ ሳይሆን ስምምነቱን ያልሰጠው ተጋቢ በህጉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ውሉ እንዲፈርስለት እስካላስደረገ ድረስ ውሉ ውጤት ያለው መሆኑን ነው፡፡ በሌላ በኩል ፀንቶ ባለ ጋብቻ ውስጥ በአንደኛው ተጋቢ በተገባ የብድር

ስምምነት የተገኘ ገንዘብ ለትዳር ጥቅም እንደዋል በህግ ረገድ ግምት የሚወሰድበት ሆኖ ይህንን ግምት የማስተባበል ግዴታ የሚወድቀው ገንዘቡ ለትዳር ጥቅም አልዋለውም በሚለው ተጋቢ ላይ እንደሆነ ከቤተሰብ ህጉ አንቀጽ 80 ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚሁ ጉዳይ ጋር በተያያዘም ይኸው ችሎት ተደጋጋሚ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በመሆኑም አመልካች ለብድር ውሉ ፈቃደኝነቴን ያልሰጠሁ በመሆኑ አላውቀውም በሚል የሚያቀርቡት መከራከሪያ የህግ መሰረት የሌለው በመሆኑ ከዚህ አንፃር የቀረበው መከራከሪያቸው ውድቅ መደረጉ በአግባቡ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሆኖም ከላይ እንደተመለከተው ተጠሪ ይኸው በብድር የተገኘው ገንዘብ ለቤት ቁሳቁስ መግዥያነት እንዲሁም ለጋብቻ ሥነ ስርዓት ማስፈፀሚያነት የዋለ ስለመሆኑ በራሳቸው የገለጹት ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት መዝገብ ያሳያል፡፡ የቤት ቁሳቁስ ከተባሉት ውስጥ ደግሞ ዋና ዋና የሚባሉት የተጠሪ የግል ንብረት ናቸው በሚል ከክፍፍሉ ውጪ እንዲሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች የተወሰነላቸው መሆኑን መዝገቡ ያሳያል፡፡ እናም ብድሩ ለቤት ቁሳቁስ መግዥያነት የዋለ ከሆነ እና እነዚሁ ንብረቶች ደግሞ የተጠሪ የግል ንብረቶች ናቸው ከተባሉ ለእቃዎቹ መግዣያነት የዋለው የብድር እዳ የጋራ የሚሆንበት የህግም ሆነ የአመክንዮ መሰረት የለም፡፡ ከዚህ አንፃር የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ለክርክር ምክንያት የሆነው እዳ "የግራ ቀኙ የጋራ እዳው ነው!" በሚል የሰጠው ውሳኔ በግራ ቀኙ የቀረበውን ክርክር ይዘት እና በብድር የተገኘው ገንዘብ የዋለበትን አገልግሎት ያላገናዘ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>**ውሳኔ**</u>

1. የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንክሰት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሠሚ ችሎት በመ/ቁ05510 በቀን 27/11/2015ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) እና በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9(1(ለ)) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. ተጠሪ ከመ/ቤቱ የተበደረው እና በሥር ፍ/ቤት የግራቀኙ እዳ ነው የተባለው የብድር ገንዘብ ተጠሪ የግል ንብረቶቹ ናቸው በሚል ለተወሰኑት ንብረቶች መግዣ የዋለ በመሆኑ እዳው የጋራ እዳ አይደለም በማለት ተወስኗል፡፡

<u>**ትዕዛዝ**</u>

<u>ማስታወሻ</u>፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

1. የዚህን ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ ካለ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ/ጋ

**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት**

*የሰ.መ.ቁ 253539*
*ጥቅምት 08 ቀን 2017 ዓ.ም*

***ዳኞች፡-*** *እትመት አሠፋ*

*ደጀኔ አያንሳ*

*ኑረዲን ከድር*

*መላኩ ካሳዬ*

*ሐብታሙ እርቅይሁን*

*አመልካች፡- ወ/ሮ ሳምራዊት ሐረሩ መንገሻ ቀርቧል*

*ተጠሪ፡- አቶ ዳኛቸው ቦካ ቡሉ ቀርቧል*

*መዝገቡ ለፍርድ የተቀጠረ ነው፡፡ በዚሁ አግባብ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡*

## ፍርድ

*የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካች መስከረም 21 ቀን 2016 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 135102 ሚያዝያ 10 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 306903 ሠኔ 28 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ብይን መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡*

*ጉዳዩ ኑዛዜን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካች ከሳሽ፣ የአሁን ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- የሟች አቶ ሀረሩ መንገሻ ልጅ እና ሕጋዊ ወራሽ ነኝ፣ አባቴ መስከረም 23 ቀን 2014 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል፣ ተጠሪ የወላጅ አባቴ ኑዛዜ ተጠቃሚ ነኝ በማለት ግንቦት 06 ቀን 1995 ዓ.ም የተጻፈ ኑዛዜ አቅርቦ በመ.ቁ 134559 የውርስ አጣሪ መዝገብ አስከፍቷል፣ በኑዛዜው ላይ በቦሌ ክፍለ-ከተማ ወረዳ 01 ውስጥ በቤት ቁጥር 5290*

**ማስታወሻ፡-** ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የተመዘገበ ቤት አመልካች እና ተጠሪ እኩል እንድንካፈል ተደርጓል፤ አባቴ የመጠጥ ሱሰኛ እና ሲጠጣ የሚያደርገውን የማያውቅ ነበር፤ የሞቱም ምክንያት መጠጥ መሆኑ በሕክምና ተረጋግጧል፤ ተጠሪ ከእኛ ጋር ኖሮ አያውቅም የሚኖረው ከእራሱ እናት እና አባት ጋር ነው፤ ወላጅ አባቴ አሳድጎት አያውቅም፤ በሰነዱ ላይ የሰፈው ፊርማ አጠራጣሪ ነው፤ አንድም የሟች ቤተሰብ በኑዛዜው ላይ በምስክርነት አልተሳተፈም፤ ስለሆነም ኑዛዜው ሊሻር ይገባዋል፤ ቁጥሩ 5290 የሆነው ቤት የአመልካች ወላጅ እናት ወ/ሮ እቴነሽ ማሞ ወልዴ እና አባቴ በጋብቻ እንደባልና ሚስት አብረው ሲኖሩ የሰሩት የጋራ ሀብት ነው፤ ኑዛዜው በእናቴ ድርሻ ላይ ጭምር የተደረገ ነው፤ በዚሁ ቤት ግቢ ውስጥም አመልካች ወላጅ አባቴ ፈቅዶልኝ በይዞታው ውስጥ ከወላጅ እናቴ በውርስ ባገኘሁት ገንዘብ ባዶ በነበረ ይዞታ ላይ ከፍተኛ ወጪ በማውጣት ሰባት ክፍል ቤት ሰርቻለሁ፤ ኑዛዜው ሊፈርስ አይገባም የሚባል ከሆነ እና ሕጋዊ ውጤት የሚኖረው ከሆነ በወላጅ አባቴ ፈቃድ በግል ጥረቴ በሰራኋቸው ቤቶች ላይ ኑዛዜው የሚያርፍበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፤ ስለሆነም ኑዛዜው እንዲሻርልኝ፤ በአመልካች ገንዘብ የተሰሩት ቤቶች ከኑዛዜው ውጪ እንዲሆኑ፤ አመልካች ከወላጅ አባቴ ከሚሰጠኝ ድርሻ ላይ ከእሩብ በላይ መቀነስ የማይችል መሆኑ ተረጋግጦ እንዲወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

ተጠሪ በሰጡት መልስ አመልካች ኑዛዜው በፈሰሰ በ 15 ቀን ጊዜ ውስጥ ስላልተቃወሙ ክሱ በይርጋ ይታገዳል፤ አመልካች ሊጣመሩ የማይችሉ ጉዳዮችን አጣምረው አቅርበዋል፤ ክሱ ንብረት እና ግንባታን የያዘ በመሆኑ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን በፍሬነገሩ ላይ በሰጡት መልስ ደግሞ አመልካች የሰጡት ምክንያት ኑዛዜን ለማስፈረስ በቂ ምክንያት አይደለም፤ በቀድሞ የሟች አሰሪ የተጻፈ ደብዳቤዎች ሟች በሙሉ አእምሮ እና የአካል ጤንነት ላይ የነበሩ ስለመሆን አለመሆናቸው ማስረጃ ሆኖ ሊቀርብ አይችልም፤ ሟች ኑዛዜውን ያደረጉት በሰነዶች ማረጋጫ እና ምዝገባ ጽ/ቤት በመሆኑ ያለምንም ጫና ኑዛዜውን ማድረጋቸውን ያሳያል፤ ምስክሮች ከኑዛዜ ተጠቃሚ ጋር ዝምድና አላቸው በሚል ብቻ ኑዛዜ ሊሻር አይችልም፤ በምስክሮች ምክንያት ኑዛዜ ሰጪ በተጽዕኖ ውስጥ እንደነበሩ አመልካች አላስረዳችም፤ ጋብቻ አለ ለማለት ያቀረበችው ማስረጃ ጋብቻ ስለመፈጸሙ አያስረዳም መስፈርቱንም አያሟላም፤ አከራካሪው ቤት ሟች በግላቸው የሰሩት ቤት ነው፤ አመልካች ምንም ዓይነት ገቢ የላትም በግቢውም ውስጥ በግል ገንዘቧ የሰራችው ቤት የለም፤ ስለሆነም የአመልካች ክስ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ተጠሪ ያቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በሚመለከት ተጠሪ ከንብረት ጋር ተያይዞ የቀረበውን ክስ በዚህ መዝገብ የሚታይ አይደለም በማለት ነሀሴ 13 ቀን 2014 ዓ.ም አመልካች ከኑዛዜ ይፍረስልኝ ጥያቄ ጋር ሌላ ንብረት ይገባኛል ይመለስልኝ ዓይነት ጥያቄ የቀረበ መሆኑን ያሳያል፤ ስለሆነም ኑዛዜ ይሻርልኝ የሚለው ዳኝነት ኑዛዜ ሊሻር ይገባል ውጤቱስ የሚሉትን ጭብጦች መደምደሚያ ላይ ከመድረስ ውጭ ተያይዥ ንብረት ይመለስ አይመለስ የሚለውን አብሮ ማየት ስለማይቻል

እና ዳኝነቱም ራሱን የቻለ ክፍያም ስለሚፈልግ ከዚህ ጉዳይ ጋር አብሮ አይታይም፤ በመሆኑም ኑዛዜ ሊሻር ይገባል ወይስ አይገባም የሚለው ክርክር ብቻ ይቀጥል፤ ንብረት ይመለስ የሚለው ጉዳይ ግን በዚህ ችሎት የሚታይ አይደለም፤ ይርጋውን በሚመለከት የቀረበው መቃወሚያ የማስረጃ እና ሕግ ጉዳዮችን የሚፈልግ በመሆኑ በማስረጃ እና በሕግ ይጣራል በማለት ብይን ሰጥቶበታል።

በመቀጠልም ኑዛዜው ሊፈርስ ይገባል? ወይስ አይገባም? ውጤቱስ ምን ሊሆን ይገባል? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ የግራቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኋላ መርምሮ ሟች አድርገውታል የተባለው ኑዛዜ በሰነዶች ማረጋገጫ እና ምዝገባ ጽ/ቤት የተደረገ በመሆኑ ሟች በዕለቱ ቀርበው ኑዛዜውን ማድረጋቸውን እና ኑዛዜው ላይ መፈረማቸው እምነት የሚጣልበት ነው፤ አመልካች ሟች ይጠጡ እንደነበር ከማስረዳት ባለፈ ኑዛዜውን ሲያደርጉ በመጠጥ ተጽእኖ ውስጥ ሆነው ውጤቱን ሳያውቁ ስለመሆኑ አላስረዱም፤ በተደጋጋሚ መጠጣት እራሱ የአእምሮ ሕመም ነው ሊባል አይችልም፤ አመልካች ኑዛዜ ከ1/4ኛ በላይ ጉዳት ያደርስብኛል ቢሉም ኑዛዜ ካረፈበት ንብረት ላይ ግማሽ 50 በመቶ አመልካች እንደሚደርሳቸው የተገለጸ በመሆኑ በገለጹት መጠን ጉዳት አይደርስባቸውም፤ ኑዛዜው ያረፈበት ቤት ምንም እንኳን ሟች ይዞታውን በፈረሰባቸው ቤት ምትክነት የተሰጣቸው ቢሆንም ሟች እና የአመልካች እናት የሆኑት እቴነሽ ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደ ባልና ሚስት አብረው እየኖሩ በጋራ የሰሩት ወይም ያፈሩት መሆኑን ድምዳሜ ላይ ተደርሷል፤ ስለሆነም የሟች ድርሻ ግማሹ ብቻ በመሆኑ በግማሽ ቤት እና ይዞታው ላይ ያደረጉት ኑዛዜ የእርሳቸው ባልሆነ ንበረት ላይ የተደረገ በመሆኑ በከፊል ሊፈርስ ይገባል ሲል ወስኗል።

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት ይግባኛቸው ተሰርዟል።

አመልካች መስከረም 21 ቀን 2016 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ሲሆን ይዘቱም፡- ወላጅ አባቴ የመጠጥ ሱሰኛ በመሆኑ የሚያደርገውን ኢያውቅም፤ በኑዛዜው ላይ የኑዛዜ አድርጊ የቅርብ ምስክሮች የሉም፤ አመልካች ኑዛዜው ሊያርፍባቸው አይገባም በማለት ክርክር ያቀረብኩባቸው ቤቶች እራሳቸውን ችለው በሌላ የክርክር አግባብ እንዲታዩ የስነ ስርዓት ሕጋችን ይከለክላል፤ አንድ ላይ አጠቃልዬ ማቅረቤ ስነ ስርዓታዊ ነው፤ አመልካች ከኑዛዜ ውጪ ይደረጉልኝ ያልኳቸው ቤቶች ለኑዛዜው ከተከፈለው ዳኝነት በተለየ ሁኔታ ዳኝነት እንዲከፍልበት ይታዘዛል እንጂ ከክርክር ውጪ ሊሆን አይችልም፤ ያስፈልጋል ቢባል እንኳን ዳኝነት እንዲከፈልበት ሊታዘዝ ከሚገባ ውጪ ከወዲሁ ውድቅ ሊደረግ አይገባም፤ በራሴ ወጪ የሰራኋቸውን ቤቶች በሚመለከት ያቀረብኩት ጥያቄ በብይን ውድቅ መደረጉ አግባብ አይደለም፤ የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች የሰራኋቸውን ቤቶች በተመለከተ የሰጡት ብይን እና ኑዛዜው እንዲፈርስ የቀረበውን ዳኝነት በተመለከተ ውድቅ በማድረግ የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል፤

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች ለክሱ ምክንያት የሆነው ኑዛዜ በግል ገንዘባቸው በሰሩት ቤት ላይ ጭምር የተደረገ መሆኑን ጠቅሰው ይኸው ንብረት ከኑዛዜው ውጭ እንዲደረግላቸው ያቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄ አስመልክቶ የስር ፍርድ ቤቶች ያለፉበት አግባብ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2/4/መ መሠረት ግራቀኙ በተገኙበት ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባው በመሆኑ ተጠሪ ቀርበው መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪ ሐምሌ 19 ቀን 2016 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት መልስ ይዘት በአጭሩ፡- የውርስ ሀብቱ ሲጣራ አመልካች ይህን ክርክር ራሳቸው አቅርበው ቤቶቹ የተሰሩት ሟች ኑዛዜ ካደረጉበት 410 ካ.ሜ ይዞታ ውጪ መሆኑ ተረጋግጦ እነዚህ ቤቶች የውርስ ሐብት ሊሆኑ አይገባም በሚል በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 134559 ሐምሌ 10 ቀን 2016 ዓ.ም ተወስኗል፤ ኑዛዜ በተደረገበት ይዞታ ላይ በአመልካች የተሰራ ቤት እንደሌለ በውርስ ይጣራልኝ መዝገብ ላይ መረጋገጡ እንደተጠበቀ ሆኖ የአመልካች አቤቱታ በፍርድ ባለቀ ጉዳዮ ላይ የቀረበ ነው፤ አመልካች ይህን ውሳኔ ሲያውቁ የሰበር አቤቱታቸውን ማቋረጥ ነበረባቸው፤ አመልካች ሰራኂቸው የሚሏቸውን ቤቶች በተመለከተ የጠየቁት ዳኝነት የታለፈው ክሶቹ ተጣምረው ሊታዩ የማይችሉ በመሆናቸው ነው፤ የስር ፍርድ ቤት ሊጣመሩ የማይችሉ ክሶችን ዳኝነት አስከፍሎ አጣምሮ ሊዳኝ አይችልም፤ አመልካች ከዚሁ ጋር በተገናኘ በተመሳሳይ ጊዜ አሁንም ድረስ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰመ.ቁ 254757 ክርክሩን መቀጠላቸው ስነ ስርኣታዊ ግድፈት ነው፤ ስለሆነም የአመልካች አቤቱታ በውርስ ይጣራልኝ መዝገብ ላይ ውሳኔ የተሰጠበት ነው በማለት ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካችም በሰጡት የመልስ መልስ አመልካች ክርክር ባቀረብኩበት ቤት ላይ ያለኝ መብት አልተከበረም፤ ተጠሪ በጠቀሱት ክርክር ላይ ውሳኔ የተሰጠልኝ ኑዛዜ ካረፈበት 410 ካ.ሜ ውጭ ያለው ንብረት ላይ ነው በማለት የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸውን ይመስላል፡፡ ይህ ችሎትም ያስቀርባል ሲባል የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

በመሠረቱ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ መሠረታዊ ዓላማ ክርክሮችን ሥርዓት ባለው መንገድ በመምራት በአፋጣኝ እንዲታዩ በማድረግ ጊዜን፣ ጉልበትን እና ገንዘብን በመቆጠብ ፍትሐዊ ውሳኔ መስጠት ነው፡፡ ፍርድ ቤቶች የተከራካሪ ወገኖችን የመደመጥ መብት ባከበረ መልኩ ክርክሩን በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሰረት የመምራት እና የመቆጣጠር ኃላፊነት ያለባቸው ሲሆን ክርክሩ በተገቢው ሁኔታ ካልተመራ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን መሠረታዊ ዓላማዎች ማሳካት ስለማይቻል የተከራካሪዎችን መብት የሚነካ ይነካል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን የሚመለከት ፍርድ ቤት ከቀረበው ዳኝነት ጥያቄ አኳያ እና ከግራቀኙ ክርክር በመነሳት ተከራካሪ ወገኖች ባልተካካዱበት ጉዳይ ላይ ውሳኔ መስጠት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

*ያለበት ስለመሆኑ፣ ተከራካሪ ወገኖች በተካካዱበት ጉዳይ ላይ ደግሞ ተገቢውን የፍሬነገር ወይም የሕግ ጭብጥ መስርቶ ማስረጃ እና ሕግን መሠረት አድርጎ ውሳኔ የመስጠት ሀላፊነት ያለበት መሆኑን፣ ጉዳዩን በይግባኝ የሚመለከተው ፍርድ ቤትም የሥር ፍርድ ቤት ክርክሩን በሥነ ሥርዓት ሕጉ በተዘረጋው ሥርዓት መሠረት መምራቱን ማረጋገጥ ያለበት መሆኑን፣ በዚህ አግባብ ተጣርቶ በአከራካሪው ጉዳይ ላይ ውሳኔ መስጠት የሚገባውም በተጠየቀው ዳኝነት ላይ በመወሰን መሆኑን ስለክርክር አመራር የተደነገጉትን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 242፣ 246፣ 247፣ 248፣ 249፣ 138፣ 257፣ 258፣ 259 181 እና 182 ድንጋጌዎች ያስገነዝቡናል፡፡*

*ከላይ የተመለከተው የፍትሐብሔር ክርክር አመራር ሒደት እንደተጠበቀ ሆኖ የሟች ውርስ ያለ ኑዛዜ፣ በኑዛዜና በከፊል ኑዛዜና በከፊል ያለ ኑዛዜ የሚፈፀም ስለመሆኑ፣ ሟች በኑዛዜ የሚያስተላልፈው ንብረትም የራሱን ንብረት ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 829 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ያስገነዝቡናል፡፡*

*በያዝነው ጉዳይ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ሟች አባታቸው አድርገውታል የተባለው ኑዛዜ እንዲሻርላቸው እና በአከራካሪው ይዞታ ላይ በግል ገንዘባቸው ሰርቻቸዋለሁ የሚሏቸው ቤቶች ከኑዛዜው ውጪ እንዲሆኑ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን በዚሁ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ላይ ተጠሪ በሰጡት መልስ ከንብረት ጋር ተያይዞ የቀረበውን ክስ በዚህ መዝገብ የሚታይ አይደለም በማለት መቃወሚያ በማቅረባቸው ችሎቱ መቃወሚያውን መርምሮ ነሀሴ 13 ቀን 2014 ዓ.ም በሰጠው ብይን አመልካች ከኑዛዜ ይፍረስልኝ ጥያቄ ጋር ሌላ ንብረት ይገባኛል ይመለስልኝ የሚል ይዘት ያለው ዳኝነት የጠየቁ ቢሆንም ኑዛዜ ይሻርልኝ የሚለው ዳኝነት ኑዛዜ ሊሻር ይገባል ወይስ አይገባም? ውጤቱስ? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ መደምደሚያ ላይ ከመድረስ ውጪ ተያያዥ ንብረት ይመለስ አይመለስ የሚለውን አብሮ ማየት ስለማይቻል እና ዳኝነቱም ራሱን የቻለ ክፍያም ስለሚፈልግ ንብረት ይመለስ የሚለው ጉዳይ በዚህ ችሎት የሚታይ አይደለም በማለት ብይን ውድቅ አድርጎ ኑዛዜውን በሚመለከት ብቻ ዳኝነት የሰጠ መሆኑን ነው፡፡ በእርግጥ ችሎቱ አመልካችዋ በአከራካሪው ቤት ይዞታ ውስጥ በግል ገንዘቤ ሰርቻቸዋለሁ የሚሏቸውን ቤቶች በተመለከተ አመልካች ከኑዛዜ ይፍረስልኝ ጥያቄ ጋር ሌላ ንብረት ይገባኛል ይመለስልኝ የሚል ይዘት ያለው ዳኝነት የጠየቁ ቢሆንም ኑዛዜ ይሻርልኝ የሚለው ዳኝነት ኑዛዜ ሊሻር ይገባል ወይስ አይገባም? ውጤቱስ? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ መደምደሚያ ላይ ከመድረስ ውጪ ተያያዥ ንብረት ይመለስ አይመለስ የሚለውን አብሮ ማየት አይቻልም በሚል በብይን ውድቅ አድርጓል፡፡ ሆኖም የንብረት መብት በሕገመንግስቱ ጥበቃ የተደረገለት መብት ከመሆኑ እና አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ሟች አባታቸው አቶ ሐረሩ መንገሻ በቦሌ ክፍለ-ከተማ ወረዳ 01 ውስጥ በሚገኘው ቁጥሩ 5290 በሆነው ቤት የአመልካችን ወላጅ እናት ድርሻ ጨምሮ እና አመልካች በወላጅ አባታቸው ተፈቅዶላቸው በግቢው ውስጥ በግል ገንዘባቸው ሰርቸዋለሁ የሚሉትን ቤት ጨምሮ ያደረጉት ኑዛዜ እንዲፈርስ ዳኝነት የጠየቁ ከመሆኑ አኳያ ከዚሁ ክርክራቸው አንጻር ኑዛዜው ታይቶ ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባ*

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ነበር፡፡ ስለሆነም ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክርክሩን በዚህ አግባብ ተረድቶ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ መስጠት ሲገባው አመልካች በአከራካሪው ቤት ግቢ ውስጥ በግል ገንዘቤ ሰርቻቸዋለሁ የሚልዋቸው ቤቶችን አስመልክቶ ያቀረቡት ዳኝነት አብሮ ሊታይ የሚችል አይደለም በማለት በብይን ውድቅ ማድረጉ፤ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንኑ ሳያርም መቅረቡ መሠረታዊ የክርክር አመራር ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 135102 ነሐሴ 13 ቀን 2014 ዓ.ም አመልካች በአከራካሪው ቤት ግቢ ውስጥ በግል ገንዘቤ ሰርቻቸዋለሁ የሚልዋቸውን ቤቶች አስመልክቶ የሰጠው ብይን እና ሚያዝያ 10 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ብይን እና ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 306903 ሠኔ 28 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ብይን በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 15/2015 አንቀጽ  መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች በአከራካሪው ቤት ግቢ ውስጥ በግል ገንዘቤ ሰርቻቸዋለሁ የሚልዋቸው ቤቶችን አስመልክቶ ያቀረቡት ዳኝነት አብሮ ሊታይ የሚችል አይደለም በማለት የሰጠው ብይን እና ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠው ብይን ተሽሯል፡፡ ከዚህ ውጪ ያለው የውሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡
3. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በውሳኔ የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ አመልካች በወላጅ አባታቸው ተፈቅዶላቸው በግቢው ውስጥ በግል ገንዘባቸው ሰርቸዋለሁ የሚሉትን  ቤት ጨምሮ ያደረጉት ኑዛዜ እንዲፈርስ ዳኝነት የጠየቁ ከመሆኑ አኳያ ከዚሁ ክርክራቸው አንጻር ኑዛዜውን በማየት የግራቀችን ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘውም ተገቢውን ትዕዛዝ በመስጠት ጉዳዩን አጣርቶ በመዝገቡ አስቀድሞ ከተሰሙት ማስረጃዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮ እና መዝኖ ተገቢ ነው ያለውን ሕጋዊ ውሳኔ እንዲሰጥበት በማለት በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(2) መሠረት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
   - መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ/ጋ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሥ/መ/ቁጥር 254153

ጥቅምት 05 ቀን 2017ዓ/ም

**ዳኞች ፡-** **ብርሀኑ አመነው**

**በዕዉቀት በላይ**

**ቀነዓ ቂጣታ**

**ብርሃኑ መንግሥቱ**

**ማርታ ተካ**

**አመልካች - ኦብሳ አመዲን**

**ተጠሪ - ፍትህ ሚኒስቴር - ዐቃቤ ሕግ --አልቀረቡም**

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ጉዳዩ በከባድ የሰዉ ግድያ ወንጀል ተጠያቂ የሚያደርጉ ግዙፋዊ ፍሬ ነገሮችን የሚመለከት ነዉ፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪ በአመልካች እና በስር ፍርድ ቤት 2ኛ ተከሳሽ በሆነዉ አህመድ ኡመር ሱሌ እና 3ኛ ተከሳሽ በሆነዉ ማህመድ (ማሜ) አብደላ ዩያ ላይ በመሠረተዉ የወንጀል ክስ - በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1/ሀ)፣35 እና 539(1/ሀ) ስር

የተደነገገዉን በመተላለፍ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ሰውን ለመግደል በማሰብ በቀን 11/05/2012 ዓ.ም በግምት ከቀኑ 10፡00 እስከ 11፡00 ሰዓት በሚሆንበት ጊዜ በድሬዳዋ ከተማ ልዩ ቦታው ጎሮ ሼክ ቡሽራ መስኪድ አካባቢ ጭካኔን በሚያሳይ መልኩ ለማ ታደሰ ባዬን በኮብልስቶን ድንጋይ ጭንቅላቱን እና ጀርባውን በመምታት ከፉኛ የአንጎል ጉዳት የራስ ቅል ስብራት እንዲደርስበት በማድረግ በዚሁ ጉዳት ህይወቱ በቀን 12/05/2012 ዓ.ም ያለፈ በመሆኑ ከባድ የሰው መግደል ወንጀል በፈፀማቸዉ ተከሰዋል የሚል ክስ መስርቶባቸዋል፡፡

አመልካች ክሱ ተነቦላቸው ወንጀሉን አልፈጸምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ክዶ ተከራክሯል፡፡ በዚህም ዐቃቤ ሕግ አንድ ምስክር አቅርቦ አሰምቶ ፍርድ ቤቱ ዐቃቤ ሕግ ካቀረበዉ የሰነድ ማስረጃ ጋር አገናዝቦ መመርመሩን በመግለጽ አመልካች በተከሰሰበት ድንጋጌ ስር ክሱን እንዲከላከል ብይን ሰጥቷል፡፡ አመልካች የመከላከያ ምስክሮችን አቅርቦ ካሰማ በኂላ ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 16947 ላይ በቀን 28/03/2015ዓ/ም በሰጠዉ ፍርድ አመልካች ከስር ተከሳሾች ጋር በመሆን ሟች በሚሄድበት መንገድ ላይ በመጠባበቅ በድንጋይ ወርዉረዉ ከመቱትና ከወደቀ በኂላ በወደቀበት ሁሉም ተከሳሾች አንዱን ከአንዱ መለየት በማያስችል ሁኔታ በግብረ አበርነት በድንጋይ በተኛበት ቀጥቅጠዉ ስለደበደቡት ሟች ከአንድ ቀን በኂላ መሞቱን በቀጥታ በዓይን ምስክር እና በህክምና እንዲሁም በገላጭ ማስረጃ በበቂ ደረጃ የተመሰከረባቸዉን አመልካች እና የስር ተከሳሾች በማስተባበል አልተከላከሉም በማለት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1/ሀ)፣35 እና 539(1/ሀ) ስር ጥፋተኛ ናቸዉ ሲል ወስኗል፡፡በመቀጠል ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት መርምሮ በሰጠዉ የቅጣት ዉሳኔ የወንጀሉን ደረጃ ደረጃ 1 እርከን 38 ላይ በማሳረፍ 5 የቅጣት ማቅለያ በመያዝ ወደ እርከን 33 ዝቅ በማድረግ አመልካች በ14 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኖበታል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ፍርድ ቤቱ በመ/ቁ 242918 ላይ በቀን 20/10/2015 ዓ.ም በቀን በሰጠዉ ዉሳኔ ተጠሪን ሳያስቀርብ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 195/1 መሠረት ሠርዞበታል፡፡

አመልካች በቀን 25/01/2016 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉ ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታዉ አጭር ይዘት፡- አመልካች የቀረበብኝ የክስ ዝርዝር ፍሬ ነገር እና የምስክር ቃል በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀፅ 539 ስር ሊያስከስሰኝም ሆነ ጥፋተኛ ሊያስብለኝ አይችልም፡፡ወንጀሉን አልፈፀምኩም እንጂ ፈፅሜ እንኳን

ቢሆን የአንቀፁ ማቋቋሚያ ፍሬ ነገር አልተሟላም፡፡ይኸዉም የቀደመ ፀብ ወይም ትውውቅ መኖሩ አልተረጋገጠም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የመግደል እቅድ ነበር ለማለት አያስችልም፡፡ የዐቃቤ ሕግ ምስክርም በነበረው ግጭት እንጂ በቂም በቀል አለመሆኑን መስክሯል፡፡ ሟች የሞተው ከሁለት ቀን በኋላ መሆኑ በነበረው ግርግር ሟች ቶሎ ህክምና ማግኘት አልቻለም እንጂ መዳን ይችል እንደነበር ያሳያል፡፡አሰቃቂ ግድያ የተፈፀመበት ቢሆን ኖሮ ሌላ ሰው ያስመለጠው መሆኑ ባልተረጋገጠበት ሟችን ያለመግደላችን የመግደል ኃሳብ ያልነበረን መሆኑን ያሳያል፡፡በሌላ በኩል ድርጊቱን ፈፅመሀል እንኳን ቢባል በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 84 እና 85 ከተጠቀሱት ማክበጃዎች ይልቅ በአንቀፅ 82 ስር ለተደነገገዉ መሰረተ ሀሳብ የቀረበ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ለሟች መሞት ትክክለኛ ምክንያት ምን እንደሆነ ባልተለየበት ሁኔታ እና ሌላ ተጨማሪ ምክንያት መኖሩ ግልፅ ባልሆነበት ሁኔታ የወንጀል አፈፃፀሙ አሰቃቂ ነው በማለት በአንቀፅ 539 ስር ጥፋተኛ መባሌ አግባብ አይደለም፡፡የዐቃቤ ሕግ ምስክር እንደ ክሱ አቀራረብ ከጥርጣሬ በፀዳ መልኩ አላስረዱም፡፡ የቀረበብን ምስክር አንድ እንደመሆኑ መጠን እና የዚህ ወንጀል መነሻ የሀይማኖት ግጭት በመሆኑ የምስክሩ ምስክርነት ከወገንተኛ የፀዳ ላይሆን እንደሚችል በመገመት በቀረበው ማስረጃ ላይ ተገቢውን ተጨማሪ ማጣሪያዎች ሊደረጉ ይገባ ነበር፡፡ምስክሩ በወንጀሉ ምክንያት እና በውጤቱ መካከል ያለውን ትስስር አላስረዳም፡፡እንዲሁም ዐቃቤ ሕግ በክሱ ላይ በኮብልስቶን እንጂ በትልቅ ድንጋይ ሟች ላይ እያነሱ ለቀቁበት ብሎ ክስ ባላቀረበበት የዐቃቤ ሕግ ምስክር ከክሱ ጋር በሚጋጭ መልኩ መስክረዋል፡፡ ይህም የምስክሩን ተዓማኒነት ጥያቄ ውስጥ የሚከት ነው፡፡በአንፃሩ መከላከያ ምስክሮቼ በአግባቡ መስክረውልኛል፡፡ስለሆነም በወንጀል ሕግ አንቀፅ 539 ስር ጥፋተኛ መባሌ አግባብ አይደለም ተብሎ ውሳኔው እንዲሻርልኝና በነፃ እንዲያሰናብት ይወሰንልኝ፡፡ ይህ የማይሆን ከሆነም ችሎቱ በተገቢው ድንጋጌ ስር የጥፋተኝነትና የቅጣት ዉሳኔ እንዲወስን በማለት አመልክቷል፡፡

ችሎቱ አቤቱታዉን መርምሮ አመልካች ፈፅሟል ተብሎ በቀረበበት ክስ ላይ የተገለፀውን የወንጀል ድርጊት አፈፃፀም ለማስረዳት በዐቃቤ ሕግ የቀረበው ማስረጃ ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 141 አንፃር ብቃት ያለው መሆን አለመሆኑን እንዲሁም አመልካች ፈፅሟል ከተባለው ድርጊት አንፃር በወንጀል ሕግ አንቀጽ 539(1/ሀ) ስር ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣቱ ተገቢ መሆን አለመሆን እንዲመረመር ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ አዝዟል፡፡ተጠሪ መጥሪያው በችሎት ደርሶት መልሱን ባለማቅረቡ መልስ የማቅረብ መብቱ ታልፏል፡፡

ከላይ አጠር ባለ መልኩ የተገለጸዉ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ውሳኔዎች እንዲሁም የአመልካች ሰበር አቤቱታን የሚመለከት ሲሆን ከፍ ሲል የተጠቀሰዉን ጭብጥ ከግምት በማስገባት የስር ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ ባሳለፈዉ የጥፋተኝነትና የቅጣት ዉሳኔ ላይ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የሕግ ስህተት መፈጸም አለመፈጸሙን እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነዉም ሕገ-ወጥነቱና አስቀጪነቱ በሕግ የተደነገገዉን አንድን የወንጀል ድርጊት ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮችን በአንድነት በሟላ መልኩ መፈጸሙ በፍርድ ቤት የተረጋገጠበት ወንጀል ፈጻሚ በወንጀል ሕጉ አግባብነት ባለዉ ድንጋጌ መሰረት ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣት ይገባዋል፡፡በዚህ መልኩ ተከሳሹ ጥፋተኛ ሆኖ ሊቀጣ የሚችለዉ በተለይም በክሱ የተጠቀሰዉን የወንጀል ድርጊት ወይም አል ድርጊት አልፈጸምኩም በማለት ክዶ ከተከራከረ በወንጀል ሕጉ ልዩ ድንጋጌዎችና በሌላ ልዩ ሕግ በተለየ ሆኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ዐቃቤ ሕግ ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮችን በሚያሳይ አግባብ ተከሳሹ ወንጀሉን ስለመፈጸሙ በማስረጃ ሲያስረዳ ነዉ፡፡ማንም ሰዉ አስቦ ወይም በቸልተኛነት በማናቸዉም ዓይነት መሳሪያ ወይም ዘዴ ሌላዉን ሰዉ መግደሉ በፍርድ ሂደት የተረጋገጠበት ሰዉ በነፍስ ገዳይነት ጥፋተኛ ሊባልና እንደአገዳደሉ ቀላልነትና ከባድነት ቅጣት ሊወሰንበት ይገባል(የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 538 ይመለከቷል) ፡፡በወንጀል ሕግ አንቀጽ 539(1/ሀ) ስር የተደነገገዉን በመተላለፍ ከባድ የሰዉ ግድያ ወንጀል ፈጽሟል በሚል የተከሰሰ ሰዉ ጥፋተኛ ተብሎ ሊቀጣ የሚችለዉ ግድያዉን ሆነ ብሎ አስቀድሞ በነበረዉ አሳብ(ቅም በመያዝ)፣ ወይም ምክንያት ሲፈጽም፤ለመግደል የተጠቀመበት መሳሪያ ወይም ዘዴ፣ የአገዳደሉ ሁኔታ ወይም ግድያዉ የተፈጸመበት ቅጣትን የሚያከብድ ጠቅላላ ምክንያት ማለትም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 84/1 ወይም 86 ስር ከተመለከቱት አካባጅ ሁኔታዎች አንጻር ሲታይ በተለይም ጨካኝ፣ነዉረኛ ወይም አደገኛ መሆኑን በሚያመላክት ሁኔታ ግድያዉን መፈጸሙ በማስረጃ ሲረጋገጥ ነዉ፡፡

ከላይ እንደተመለከተዉ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 539(1/ሀ) ስር “... በተለይ ጨካኝ፣ነዉረኛ ወይም አደገኛ መሆኑን በሚገልጽ ሁኔታ...” የሚሉ ገላጭ ቃላት ጥቅም ላይ የዋሉት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 84/1 ቅጣትን የሚያከብዱ ጠቅላላ ምክንያቶች ናቸዉ በሚል ከተገለጹት እና በሕጉ በግልጽ ያልተጻፈ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 86 ስር እንደተደነገገዉ ሌላ በቂ ማክበጃ ምክንያቶች ሲያጋጥም የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 539(1/ሀ) ተፈጻሚ እንደሚሆን በማመላከት የተደነገገ ነዉ፡፡በዚህ መሰረት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 539(1/ሀ)፣84/1 እና 86 ስር የተደነገገዉ በጣምራነት ሲነበብ የድርጊቱ ፈጻሚ“...በተለይም ጨካኝ፣ነዉረኛ ወይም አደገኛ መሆኑን...” የሚያሳይ ከሆነና ከማክበጃ

ምክንያቶቹ አንዱ ሲኖር የግድ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 539(1/ሀ) ድንጋጌ ስር ተጠያቂ እንደሚሆን ወይም የግድያ ወንጀሉን ይበልጥ ከባድ የሚያደርግ ሁኔታ ሆኖ ጥቅም ላይ የዋለ አገላለጽ እንደሆነ ከድንጋጌዉ ይዘትና መንፈስ መገንዘብ ይቻላል፡፡ከዚህ ጋር በተያያዘ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 45927 (በቅጽ 10 እንደታተመዉ) እና 97203(በቅጽ 17 እንደታተመዉ) ላይ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 539(1/ሀ) ስር የተመለከቱት የወንጀሉ ማቋቋሚያ አላባዎች (elements) በየራሳቸው መቆም የሚችሉ እንደሆኑ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

የወንጀል ሕጉን አንቀፅ 539(1/ሀ) እና 540 አንድነትና ልዩነት በተመለከተ በሠ/መ/ቁጥር 97203(ቅጽ 17) ፣232712 እና 237436(ያልታተሙ) መዛግብት ላይ በተሰጠዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ላይ እንደተመለከተዉ በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 539 እና 540 መሠረት የሚፈፀሙ ግድያዎች ሆነ ተብሎ ወይም በማወቅ (ታስቦ) የሚፈጸሙ ናቸው፡፡ በዚህ ረገድ ሁለቱ አንቀፆች ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ ነገር ግን ሁለቱን አንቀፆች የተለያዩ የሚያደርጓቸው መሰረታዊ ነጥቦች መኖራቸውን ከድንጋጌዎቹ ይዘት መረዳት ይቻላል፡፡ አንድ ሰው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 539(1/ሀ) መሠረት ጥፋተኛ እንዲሆን በዚሁ አንቀጽ የተጠቀሱት ሁኔታዎች ተሟልተው መገኘት አለባቸው፡፡ከእነዚህ ሁኔታዎች አንጻር ተከሳሹን ድርጊቱን ለመፈፀም ካነሣሣው ሃሣብ እና ከድርጊቱ አፈፃፀም አንፃር በመመርመር የድንጋጌውን ትክክለኛ አፈጻጸም መለየት ይገባል፡፡በወንጀል ሕግ አንቀጽ 539(1/ሀ) መሰረት የተከሰሰ ሰዉ ጥፋተኛ ተብሎ እንዲቀጣ ሊሟሉ የሚገባቸዉን መሰረታዊ አላባዎች ከላይ ተመልክተናል፡፡ በሌላ በኩል ተከሳሹ ግድያዉን የፈጸመዉ ቀድሞ ግድያዉን ለመፈጸም አስቦና ተዘጋጅቶ ሳይሆን በዕለታዊ ጸብ እና አለመግባባት ምክንያት እና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 541 ስር ከተደነገጉት ሁኔታዎች ዉጭ በሆነ ሁኔታ የፈጸመዉ ሲሆን በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 540 መሰረት ተራ በሆነ የሰዉ ግድያ የሚያስጠይቅ ይሆናል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች ከሌሎች የስር ተከሳሾች ጋር በመሆን ሟች በሚሄድበት መንገድ ላይ በመጠባበቅ በድንጋይ ወርዉረዉ ከመቱትና ከወደቀ በኋላ በወደቀበት ሁሉም ተከሳሾች አንዱን ከአንዱ መለየት በማያስችል ሁኔታ በግብረ አበርነት በድንጋይ በወደበት (በተኛበት) ቀጥቅጠዉ ስለደበደቡት ሟች ከአንድ ቀን በኋላ መሞቱን በቀጥታ በዓይን ባየ ምስክር ፣ በህክምና እና በገላጭ ማስረጃ እንደተረጋገጠ ማስረጃ የመመርመርና የመመዘን ሥልጣን የተሰጠዉ የስር ፍርድ ቤት ማስረጃዎችን መርምሮና መዝኖ ያረጋገጠዉ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡አመልካች በዚህ መልኩ የተመሠከረበትን ለማስተባበል አቅርቦ ያሰማቸዉ ምስክሮች አመልካች ወንጀሉ በተፈጸመበት ጊዜ ወንጀሉ በተፈጸመበት ቦታ እንዳልነበር በመግለጽ ቢመሰክሩም የምስክሮቹ ቃል እና ከቀበሌ

የመጣዉ ማስረጃ ተአማንነት እንደሌለዉ በመግለጽ የስር ፍርድ ቤት አመልካች በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ የተመሰከበትን አላስተባበለም የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ከዚህ አንጻር የስር ፍርድ ቤት በደረሰበት ድምዳሜ የማስረጃ ምዘና መርህ አተገባበር አንጻር በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚያስብል በቂ ምክንያት አልተገኘም፡፡

በመለቀጠል ከላይ በተገለጸዉ መሠረት በማስረጃ የተረጋገጠዉን ከግምት በማስገባት አመልካች በሟች ግድያ ላይ የነበረዉ ተካፋይነት ደረጃ አመልካችን በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 539(1/ሀ) መሠረት ጥፋተኛ የሚያደርገዉ ነዉ ወይስ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 540 ስር ጥፋተኛ የሚያደርገዉ ነዉ? የሚለዉን መርምረናል፡፡ አመልካች ሟችን ከሌሎች ግብረ አበሮቹ ጋር ሟች በሚሄድበት መንገድ ላይ በመጠበቅ በድንጋይ መትተዉ ጥለዉት በወደቀበት ደጋግመዉ በድንጋይ በመምታት እንደገደሉት ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ከግብረ አበሮቹ ጋር ሟች በሚሄድበት መንገድ ላይ ጠብቆ ወንጀሉን መፈጸሙ ወንጀሉን ለመፈጸም አስቀድሞ እንዳሰበ የሚያሳይ ነዉ፡፡ እንዲሁም ሟችን ከግብረ አበሮቹ ጋር በድንጋይ መትቶ ከጣለዉ በኋላ በወደቀበት ደጋግሞ በድንጋይ መምታቱ ጨካኝነቱንና አደገኛነቱን በሚያሳይ መልኩ ወንጀሉን መፈጸሙን ያሳያል፡፡

ሲጠቃለል አመልካች ሟችን ለመግደል ፍጹም ፈቃደኛ በመሆን ጨካኝነቱን በሚያሳይ መልኩ ከሌሎች ግብረ አብሮቹ ጋር በድንጋይ ደብድቦ መግደሉ ስለተረጋገጠ የወንጀሉ አፈጻጸምም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 84(1/ሀ) እና 539(1/ሀ) ስር የተደነገገዉን ማክበጃ ምክንያት የሚያሟላ ነዉ፡፡በመሆኑም አመልካች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 539(1/ሀ) ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ በመባሉ የተፈጸመ ስህተት የለም ብለናል፡፡እንዲሁም አመልካች ከቅጣት ዉሳኔ አንጻር ስህተት ተፈጽሟል በሚል ያቀረበዉ ቅሬታ ካለመኖሩም በተጨማሪ በቅጣት ዉሳኔዉ ላይ ችሎቱ ያገኘዉ ስህተት የለም፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ዉሳኔ

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 16947 ላይ በቀን 28/03/2015ዓ/ም እና በቀን 06/04/2015 ዓ/ም የሰጠዉ የጥፋተኝነትና የቅጣት ዉሳኔ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 242918 ላይ በቀን 20/10/2015 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 መሰረት ጸንተዋል፡፡

## ትዕዛዝ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ዉሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

- የዉሳኔዉ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት እና አመልካች ታስሮ ለሚገኝበት ማረሚያ ቤት ይተላለፍ፡፡ ሲጠይቁ ለግራ ቀኙም ይሰጣቸዉ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰመ.ቁጥር 254266

ጥቅምት 06ቀን 2017ዓ/ም

**ዳኞች፡-** እትመት አሠፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

ሐብታሙ እርቅይሁን

አመልካች፡- አቶ ኦሊያድ ታምሬ -ተወካይ ፍራኦል ታምሬ -ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ኤፍሬም ታምሬ -ቀረቡ

መዝገቡ ለፍርድ የተቀጠረ ነው፡፡ በዚሁ አግባብ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካች ጥቅምት 19 ቀን 2016 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 104645 ግንቦት 17 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 303951 ሐም 26 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል በሚል አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ ልጅነትን በመቃወም የቀረበን አቤቱታ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካች የመቃወም አመልካች፤ የአሁን ተጠሪ ደግሞ የመቃወም ተጠሪ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁን አመልካች በስር ፍርድ ቤት

*ባቀረቡት የመቃወም አቤቱታ ሟች አቶ ታምሬ ጋረደው ከአመልካች እና የሟች ሕጋዊ ባለቤት ጋር ከ 40 ዓመታት በላይ በትዳር አብረው ሲቆዩ ተጠሪን አይተናቸው አናውቅም፤ ሟችም ሌላ ልጆች ያልዋቸው ስለመሆኑ ለማንም ተናግረው አያውቁም፤ ፍርድ ቤቱ የሰጠው ውሳኔ መብቴን የሚነካ በመሆኑ ካቀረብኳቸው ማስረጃዎች በተጨማሪ የዘረመል ምርመራ እንዲደረግ እና ተጠሪ ከሟች መምህር ታምሬ ሳይወለዱ እና የደም ግንኙነት ሳይኖራቸው ከአዲስአበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 59349 በቀን 04/08/2014 ዓ.ም የተሰጣቸው የወራሽነት ሰርተፍኬት እና በመ.ቁ 104645 በቀን 27/12/2014 ዓ.ም ያገኙት የልጅነት ማረጋገጫ ውሳኔ ያላግባብ የተገኘ ውሳኔ ስለሆነ ይሰረዝልኝ የሚል ነው፡፡*

*ተጠሪ በሰጡት መልስ የሟች ወላጅ አባቴ አቶ ታምሬ ጋረደው ከወ/ሮ ሙሉእመቤት ስመኝ ጋር ከመጋባታቸው በፊት ከወላጅ እናቴ ወ/ሮ አስቻለች ተፈራ ጋር በሚማሩበት ጊዜ በነበራቸው የፍቅር ግንኙነት ተወልጃለሁ፤ አባቴም ልጅነቴን ተቀብሎ በሕይወት እያለ እንጠያየቅ ነበረ፤ የመቃወም አቤቱታው በሀሰት የቀረበ ነው፤ የዘረመል ምርመራን አስመልክቶ አመልካች የአባቴ ልጅ መሆኑን የማላምንበት በመሆኑ ምርመራው ከአመልካች ጋር ሊደረግ አይገባም፤ በአመልካች ወጪ ከአባቴ አስክሬን ላይ ናሙና ተወስዶ ምርመራ ሊደረግ ስለሚገባ እቃወማለሁ በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡*

*ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የግራቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኋላ መርምሮ የአመልካች ምስክሮች ሟች በሕይወት እያሉ ተጠሪ ልጃቸው እንደሆነ ያልነገሯቸው እና እነሱ ከሚያወቋቸው ልጆቸች ውጨ ሌላ ልጅ እንዳላቸው ነግረዋቸው የማያውቁ እንዲሁም ተጠሪንም የማያውቋቸው ስለመሆኑ እንጂ ሟች አቶ ታምሬ ሌላ ልጅ ሊኖራቸው የማይችል እና ተጠሪ በእርግጥም ከሟች አቶ ታምሬ ጋረደው የማይወለዱ ስለመሆናቸው በሚያረጋግጥ መልኩ ያላስረዱ በመሆኑ የሟች አቶ ታምሬ ጋረደው ልጅ አይደሉም ወደ ሚል ድምዳሜ አያደርስም፤ የአመልካች የሰነድ ማስረጃ በእድር እና በቤተሰብ ማሕደር ላይ የተጠሪ ስም ተመዝግቦ እንደማይገኝ የሚያሳይ ከመሆኑ በቀር ተጠሪ ከሟች ታምሬ ሊወለዱ የማይችሉ ስለመሆናቸው እንደበቂ ማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ አይችልም፤ በአንጻሩ ተጠሪ የሟች አቶ ታምሬ ልጅ እንደሆነ እና ከተጠሪ እናት ጋር ተማሪ እያሉ በነበራቸው የፍቅር ግንኙነት የተወለዱ ስለመሆኑ የመገለጹ እና በተለይም ሟች ተጠሪ ልጃቸው እንደሆነ አምነው ይጠይቁት እንደነበር ልጄ ነው ብለው እንዳስተዋወቋቸው መስክረዋል፤ ይህም ሟች ተጠሪው ልጃቸው እንደነበር በራሳቸው ተቀብለው የነበረ መሆኑን የሚያሳይ ነው፤ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 154 የአንድ ሰው የልጅነት ሁኔታ በልደት ምስክር ወረቀት ሊረጋገጥ የሚችል ስለመሆኑ ተደንግጓል፤ ተጠሪ በምስክሮች የሟች ልጅ መሆናቸውን ያስረዱ ሲሆን ከዚሁ ጋር በሚስማማ መልኩ ተጠሪ የልደት የምስክር ወረቀትም ያላቸው ስለመሆኑ ተረጋግጧል፤ ስለሆነም አስቀድሞ የተሰጠውን የልጅነት ውሳኔ ሊያሻር የሚያስችል በቂ ምክንያት አልተገኘም በማለት የመቃወም አቤቱታውን ውድቅ አድርጎታል፡፡*

**ማሳ ታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!**

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም ይግባኛቸው ተቀባይነት አላገኘም፡፡

አመልካች ጥቅምት 19 ቀን 2016 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይህን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ሲሆን ይዘቱም፡- የዘረመል ምርመራ እንዲደረግ ጠይቂ ምንም ሳይባል ታልፏል፤ አባትነት በፍርድ ሊነገርባቸው በሚችላቸው ሁኔታዎች የዘረመል ምርመር በማስተባባያነት ሊቀርብ ይችላል፤ አመልካች የሟች ልጅ መሆኔ እና የመካድ ክስ ለማቅረብ መብት ያለኝ ስለመሆኑ የጸና እና ያልተሻረ ውሳኔ አለኝ፤ አመልካች የመካድ ክሱን ካቀረብኩ በኂላ ፍርድ ቤቱ ሟች አባቴን ተክቼ ክሱን ለማቅረብ የሚያስችል ጥቅምና ግንኙነት ያለኝ መሆኑን አምኖ በብይን አረጋግጦ ክርክሩ እንዲቀጥል አዝዞ ሳለ ተጠሪ ልጅነታቸውን እጠራጠራለሁ በማለታቸው ብቻ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሟች በሌሉበት የዘረመል ምርመራውን ማዘዝ አይቻልም ሲል የሰጠው ውሳኔ ሰበር ሰሚ ችሎቱ በሰ.መ.ቁ 101345 በቅጽ 8 ላይ የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በመተላለፍ የተሰጠ ውሳኔ ነው፤ ስለሆነም ይህ ታልፎ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የስር ፍርድ ቤት አመልካች የዘረመል ምርመራ እንዲደረግ እና ውጤቱ እንዲቀርብ ባቀረቡት ክርክር ላይ ተገቢውን ብይን/ትዕዛዝ ሳያሳርፍ ተጠሪ የልጅነት ሁኔታ ያላቸው መሆኑን ከአመልካች በተሻለ ሁኔታ አስረድተዋል በማለት የአመልካችን የመቃወም አቤቱታ ውድቅ ማድረጉ የግራቀኙን አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎች አጠቃሎ በመመርመር እና በመመዘን የደረሰበት መደምደሚያ ነው የሚያስብል ነውን? ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዘረመል ምርመራ አባትነትን በፍርድ ለማስወሰን የሕግ መጠየቅ ሆኖ የሚቀርብ አይደለም በማለት ያስቀመጠው መደምደሚያ በሰ.መ.ቁ 152777 የቤተሰብ ሕጉን አንቀጽ 144(ሀ) ድንጋጌን መሠረት በማድረግ የተሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሠረት ያደረገ ነውን? የሚሉትን ጭብጦች ለማጣራት ሲባል ተጠሪ ቀርበው መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪ ሰኔ 18 ቀን 2016 ዓ.ም በሰጡት መልስ ተጠሪ ከሟች መምሬ ታምሬ ጋረደው እና ከእናቴ ከወ/ሮ አስቻለች ተፈራ በነበራቸው የፍቅር ግንኙነት የተወለድኩ ሲሆን ወላጅ አባቴ ልጁ መሆኔን ተቀብሎ ተንከባክቦ አሳድጎኛል አስተምሮኛል፤ ይህንኑንም በማስረጃ አረጋግጫለሁ፤ አመልካች ተጠሪን አይተነው አናውቅም ሟችም ነግረውን አያውቁም ከማለት በቀር የሟች ልጅ አይደለም ሊያስብል የሚያስችል ማስረጃ አላቀረበም፤ ልጅነት በሁኔታ ሊረጋገጥ ይችላል፤ የዘረመል ምርመራ የሚያስፈልገው እና ሊደረግም የሚችለው ልጅ ነኝ ወይም ተወላጅ ነኝ የሚለው አካል ከሟች ስለመወለዱ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሲያቀርብ ነው፤ የዘረመል ምርመራው የሚደረገው ከማን ጋር ነው የሚለው ነጥብ ወሳኝ ነጥብ ነው፤ አስከሬን ቆፍሮ ተደርጎ ከአጽማቸው ምርመራ ከሚደረግ በቀር ተጠሪ እና አመልካች ከአንድ እናት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማ አያገለግልም!

*የማንወለድ እና በአባት ብቻ የምንገናኝ በመሆኑ የአባቴ ልጅ መሆኑንም የማላምነበት በመሆኑ የሟች ልጆች ነን ከሚሉ ተለይቶ ለብቻው ምርመራው እንዲደረግ የሚያቀርበው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፤*

*አመልካችም ፍርድ ቤቱ ካመነበት እና ለትክክለኛ ፍትሕ አሰጣጥ ይረዳል ብሎ ካመነ ናሙናው ተጠሪ ከመረጡት ከሌሎች የሟች ሕጋዊ ልጆች በመጨረሻም ከአባቴ መካነ መቃብር ተወስዶ ቢደረግ ተቃወሞ የለኝም በማለት የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡*

*የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸውን ይመስላል፡፡ ይህ ችሎትም ያስቀርባል ሲባል የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡*

*በመሠረቱ ግራቀኝ ተከራካሪ ወገኖች እንደ የክርክራቸው ለማስረዳት ያስችሉናል የሚሏቸውን የሠውም ሆነ የጽሁፍ ማስረጃዎችን ዝርዝርና ዋናውን ወይም ትክክለኛ ግልባጮቻቸውን ማቅረብ ያለበት ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 222፤ 223 እና 234 ድንጋጌዎች ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ የግራ ቀኙ ክርክር በቃል ተሰምቶና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 246፣ 247፣ 248 እና 249 ድንጋጌዎች አግባብ ተገቢው ጭብጥ ተይዞ ለጉዳዩ በሕጉ አግባብ የቀረቡት የተከራካሪ ወገኖች ማስረጃዎች ተሰምተውና አስፈላጊ ሲሆንም በሕጉ አግባብ ፍርድ ቤቱ ተጨማሪ ማስረጃዎችን እንዲቀርቡ በማድረግ ጉዳዩን በሚገባ አጣርቶ እውነትን መሰረት ያደረገ ፍትሐዊ ዳኝነት መስጠት ያለበት መሆኑን፤ በሕግ አግባብ የቀረበን ማስረጃ ከማስረጃው አግባብነት፣ ተቀባይነት እና የማሳመን ብቃት አንጻር በማየት የማይቀበለው ሆኖ በመገኘቱ ምክንያት ሳይመለከተው የቀረ ካልሆነ በቀር ክርክርን በማስረዳት የቀረበን የተከራካሪ ወገን ማስረጃ በዘፈቀደ ውድቅ ማድረግ እንደማይችል ስለማስረጃ አቀባበል በተደነገጉት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 138፣ 257፣ 258 እና 259 ድንጋጌዎች ስር በግልጽ ተመልክቷል፡፡ እንዲሁም ክርክርን ለማስረዳት የቀረበን፤ የተሰማን ማስረጃ አንድ በአንድ በማገናዘብ በመተቸት፤ የሚቀበለውንና የማይቀበለውን በመለየት ዳኝነት መስጠት እንደሚገባቸው እና ይህ የማስረጃ አቀባበል ሂደትም በፍርድ አጻጻፍ ወቅት የግድ ሊከተሉት የሚገባ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 181 እና 182 ድንጋጌዎች ይዘት ያስገነዝቡናል፡፡*

*በተሻሻለው የፌዴራል ቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 መሰረት አባትነት የሚረጋገጥባቸው ሶስት መንገዶች ያሉ ሲሆን እነዚህም መንገዶች በቅደም ተከተል የተደነገጉ ናቸው፡፡ በዚሁ ሕግ በቅድሚያ የተቀመጠው በሕግ የታወቀ ግንኙነት /ጋብቻ እና ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነትን/ አስመልክቶ ክርክር የተነሳበት ልጅ በዚህ ግንኙነት ውስጥ በሕግ በታወቀው የእርግዝና ጊዜ መወለዱን መነሻ በማድረግ የልጁ አባት ባልየው ወይም ከልጁ እናት ጋር ከጋብቻ ውጪ አብሮ የሚኖረው ሰው ነው ተብሎ ሕጉ ግምት የሚወስድበት ነው፡፡ ይህ የሕግ ግምት በማስረጃ መረጋገጥ በሚገባቸው ፍሬ ነገሮች ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ እነዚህን ፍሬ ነገሮች ማረጋገጥ የቻለ ወገን ሌላ የተለየ ማስረጃ ማቅረብ*

ሳይጠበቅበት ሕጉ በእራሱ በወሰደለት ግምት መሰረት ከልጁ እናት ጋር በሕግ በታወቀ ግንኙነት የኖረው ወንድ የልጁ አባት መሆኑ ይረጋገጣል፡፡

በሕጉ የተመለከተው ሌላኛው የአባትነት ማረጋገጫ መንገድ በሕግ የታወቀ ግንኙነት ማለትም ጋብቻ እና ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት የመኖር ግንኙነት ሳይኖር የተወለደን ልጅ አንድ ሰው አባት ነኝ በሚል በጽሑፍ ያወቀ እንደሆነ በዚሁ ስርዓት አባትነትን ማረጋገጥ የሚቻል ስለመሆኑ፤ ከላይ በተቀመጡት ሁኔታዎች በማይሸፈኑ በአዋጁ አንቀፅ 143 የተዘረዘሩት ምክንያቶች ባጋጠሙ ጊዜ ደግሞ እንደ ሶስተኛ የአባትነት ማረጋገጫ መንገድ አባትነት በፍርድ የሚነገርበት አግባብ በቤተሰብ ሕጉ ተመልክቶአል፡፡ በዚህ አግባብ በሚረጋገጥ የአባትነት ውሳኔ ላይ የዲ.ኤን.ኤ ምርመራ አባትነትን ለማስተባበል መቅረብ የሚችል ስለመሆኑ በአንቀጽ 144 ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 152100 እና በሌሎችም መዛግብት በሰጠው ውሳኔ አባትነትን በፍርድ ለማረጋገጥ የሚቀርብ ክስን ለማስተባበል መቅረብ የሚገባቸው ማስረጃዎች በቤተሰብ ሕጉ በአንቀጽ 144 ላይ እንደተመለከተ፤ በአንቀጽ 144 (ሐ) ድንጋጌ መሰረት የዲ.ኤን.ኤ. ምርመራ ከእነዚህ መካከል የሚጠቀስ መሆኑን፤ ፍርድ ቤቱ ለክርክሩ አወሳሰን አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በራሱ አነሳሽነትም ቢሆን ምርመራው እንዲከናወን ትዕዛዝ መስጠት የሚችል መሆኑን በመግለጽ በየትኛውም እርከን ላይ ለሚገኙ ፍርድ ቤቶች አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ የሟች መምሬ ታምሬ ልጅ ነኝ በማለት ያስወሰኑት ሟች ከእናታቸው ጋር በነበራቸው የፍቅር ግንኙነት ተወልጃለሁ በሚል ሲሆን አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 መሠረት በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት የመቃወም አቤቱታ ፍርድ ቤት ባቀረቡት የመቃወም አቤቱታ የጠየቁት ዳኝነት ተጠሪ ከሟች መምህር ታምሬ ሳይወለዱ እና የደም ግንኙነት ሳይኖራቸው ከአዲስስአበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 59349 በቀን 04/08/2014 ዓ.ም የተሰጣቸው የወራሽነት ሰርተፍኬት እና በመ.ቁ 104645 በቀን 27/12/2014 ዓ.ም ያገኙት የልጅነት ማረጋገጫ ውሳኔ እንዲሰረዝ የሚል ነው፡፡ ይህንኑ ክርክራቸውን ለማስረዳትም የዘረመል ምርመራ እንዲደረግ ጠይቀዋል፡፡ አመልካች የዘረመል ምርመራ እንዲደረግ የጠየቁ ቢሆንም ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዘረመል ምርመራው ምርመራ እንዲደረግ የቀረበውን ጥያቄ በዝምታ  ያለፈው ሲሆን ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ደግሞ የዘረመል ምርመራ አባትነትን በፍርድ ለማስወሰን የሕግ መጠየቅ ሆኖ የሚቀርብ ባለመሆኑ እና የተጠሪ አባት ስለመሆናቸው በፍርድ ውሳኔ የተሰጠባቸው አቶ ታምሬ ጋረደው በሕይወት የሌሉ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት የዘረመል ምርመራ እንዲደረግ ትዕዛዝ አለመስጠቱ የሚነቀፍ አይደለም በማለት በሚል ውድቅ አድርጎታል፡፡

አመልካች ተጠሪው የሟች ልጅ እና ወራሽ እንደሆኑ በመግለጽ የተሰጠው ውሳኔ እንዲሰረዝ መቃወሚያ ሲያቀርቡ የዲ.ኤን.ኤ ምርመራ እንዲደረግ እስከተጠየቀ ድረስ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ሊሰጥ የሚገባው የዘረመል ምርመራው እንዲደረግ ትዕዛዝ ከተሰጠ እና ውጤቱ ከቀረበ በኋላ ነው፡፡ ስለሆነም ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ምርመራው እንዲደረግ ትዕዛዝ በመስጠት ውጤቱ ከቀረበለት በኋላ መወሰን ሲገባው በዝምታ ማለፉ፣ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የዘረመል ምርመራ አባትነትን በፍርድ ለማስወሰን ሊጠየቅ አይችልም በማለት ውድቅ በማድረግ የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዘረመል ምርመራው ከሟች መምሬ ታምሬ ጋረደው አስከሬን ወይም ተጠሪ የሟች ልጆች ስለመሆናቸው ካመነባቸው ሌሎች ልጆች ናሙና ተወስዶ እንዲመረመር እና ውጤቱ ከቀረበለት በኋላ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ እንዲሰጥበት ማድረግ ፍትሐዊ እና ሥነ ሥርዓታዊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 104645 ግንቦት 17 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 303951 ሐምሌ 26 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በውሳኔ የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው መንገድ የዘረመል ምርመራው ከሟች መምሬ ታምሬ ጋረደው አስከሬን ወይም ተጠሪ የሟች ልጆች ስለመሆናቸው ካመነባቸው ሌሎች ልጆች ናሙና ተወስዶ እንዲመረመር እና ውጤቱ ከቀረበለት በኋላ ተገቢውን ሕጋዊ ውሳኔ እንዲሰጥበት በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/2(ለ) መሠረት ጉዳዩን መልሰንለታል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. መጋቢት 25 ቀን 2016 ዓ.ም በመዝገቡ የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
   - መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሠ/መ/ቁጥር 254672

ጥቅምት 25 ቀን 2017ዓ/ም

**ዳኞች ፡- ብርሃኑ አመነው**

**በዕዉቀት በላይ**

**ቀነዓ ቂጣታ**

**ብርሃኑ መንግሥቱ**

**ማርታ ተካ**

**አመልካች፡- አቶ ተሾመ ተሰማ**

**ተጠሪ ፡- አቶ ታደሰ ወጀሮ**

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ አንድ ዳኛ በተዋረድ በሚገኙ ሁለት ፍርድ ቤቶች በአንድ ጉዳይ ተሰይሞ የሚሰጠዉ ዉሳኔ የሚኖረዉን ሕጋዊ ዉጤት የሚመለከት ነው፡፡ክርክሩ የተጀመረው በማርቃ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች በተጠሪ ላይ በመሰረቱት ክስ በስማቸዉ ተመዝግቦ ከሚገኘዉ የመሬት ይዞታ ላይ ተጠሪ 0.35 ሄክታር መሬት በጉልበት ይዘዉ እንዳልጠቀም ስለከለከሉኝ እንዲለቁ ይወሰንልኝ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪ ደግሞ የአመልካችን የመሬት ይዞታ አልያዝኩም በማለት ክደዉ ተከራክረዋል፡፡

የወረዳዉ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 20139 ላይ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃዎችን መርምሮ በቀን 10/01/2015ዓ/ም በዋለዉ ችሎት በሰጠዉ ዉሳኔ ተጠሪ ሁከት በመፍጠር የአመልካችን 1.102 ሄክታር መሬት መያዛቸዉን ማረጋገጡን በመግለጽ እንዲለቁላቸዉ ወስኗል፡፡ተጠሪ በዉሳኔዉ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለዳዉሮ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን በመ/ቁጥር 16906 ላይ አከራካሮ ሦስተ ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት በቀን 18/04/2015ዓ/ም በዋለዉ ችሎት በሰጠዉ ዉሳኔ የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ አጽንቷል፡፡

በመቀጠል ተጠሪ ይግባኝ ለደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዉ ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 18197 ላይ ግራ ቀኙን በማከራከር በቀን 14/11/2015ዓ/ም በዋለዉ ችሎት ሦስት ዳኞች በተሰየሙበት በሰጠዉ ዉሳኔ ተጠሪ የያዙት የአመልካች ይዞታ 0.35 ሄክታር ነዉ በማለት አሻሽሎ ወስኗል፡፡በዚህ መሰረት በዳዉሮ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሦስተኛ ተራ ቁጥር የተሰየሙት ዳኛ እና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በ2ኛ ተራ ቁጥር የተሰየሙት ዳኛ አንድ ሰዉ ናቸዉ፡፡በዚህ መልኩ በተለያዩ ፍርድ ቤቶች አንድ ዳኛ መሰየማቸዉን እና ዉሳኔዉ በመሻሻሉ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም ችሎቱ በመ/ቁጥር 18556 ላይ በቀን 21/02/2016ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ አንድ ዳኛ በከፍተኛ ፍርድ ቤት እና በጠቅላይ ፍርድ ቤት ተሰይመዉ የወሰኑ ቢሆንም ዳኛዋ በሁለት ፍርድ ቤት መሠየማቸዉ ምክንያት በአመልካች መብት ወይም ጥቅም ላይ ያስከተለዉ ጉዳት ምን እንደሆነ አመልካች ካለማስረዳታቸዉም በተጨማሪ በዉሳኔዉ ላይ የሚያመጣዉ ለዉጥ የለም በማለት ከስረ ነገሩ አንጻር የተሰጠዉ ዉሳኔም ቢሆን በተጠሪ የተያዘዉ የመሬት ይዞታ በባለሙያ ተጣርቶ የተወሰነ በመሆኑ የተፈጸመ ስህተት የለም በማለት ተጠሪን ሳያስቀርብ ሠርዞባቸዋል፡፡

አመልካች በቀን 30/02/2016 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታቸዉ አጭር ይዘት፡- የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ ሰሚነት ስልጣኑ የወረዳው ፍርድ ቤት ከሰጠው ውሳኔ የተለየ ውሳኔ ባልሰጠበት ሁኔታ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት 2ኛ ይግባኝ ስልጣን ሳይኖረው ሁለተኛ ይግባኝ ተቀብሎ መወሰኑ ስህተት ነዉ፡፡ ተጠሪ 1.102 ሄክታር የሚሆን

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

መሬትን ወደ አመልካች ሕጋዊ ይዞታ በጉልበት ገብተዉ መያዛቸዉ በምስክሮች ቃል በባለሙያ እና በሰነድ ማስረጃ ጭምር ተረጋግጦ እያለ ይህንን አልፎ በተጠሪ የተያዘዉ 0.35 ሄክታር ብቻ ነዉ ሲል የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ በሰ/መ/ቁጥር 207003 ላይ የተሰጠዉን የሚቃረን በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ክርክር የተነሳበትን ጉዳይ ክብርት ዳኛ ወይንሸት ግደይ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዳኝነት አይተውት በታየዉ ይግባኝ የወረዳውን ፍርድ ቤት ውሳኔ በመጀመሪያዉ ይግባኝ አይተዉ እንዲጸና ወስነዋል፡፡በመቀጠል በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት 2ኛ ይግባኝ ላይ በድጋሚ ከሌሎች ዳኞች ጋር በዳኝነት ተሰይመዉ ጉዳዩን አይተውት ውሳኔው እንዲሻሻል ወስነዋል፡፡

አመልካች አንድ ዳኛ ቀድሞ በዳኝነት ያየውን ጉዳይ በድጋሜ ሲመጣለት በሕጉ መሰረት ከችሎት መነሳት ያለበት መሆኑን በመገንዘብ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረብኩ ቢሆንም ችሎቱ አቤቱታዬን ከሕግ ውጭ ውድቅ አድርጎታል፡፡ ይህም በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 13/2015 አንቀጽ 24(1/ሐ) ስር ክርክር የተነሳበትን ጉዳይ አስቀድሞ በዳኝነት ያየው ዳኛ ከችሎት መነሳት እንዳለበት የተደነገገዉን የሚቃረን በመሆኑ ዉሳኔዉ ተሽሮ የወረዳዉ እና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ ይጽናልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

ችሎቱ አቤቱታዉን መርምሮ የዳውሮ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በይግባኝ ባየበት ጊዜ በዳኝነት ተሰይመዉ የወረዳዉን ፍርድ ቤት ውሳኔ ያጸኑት ዳኛ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በይግባኝ ሲመለከት በድጋሚ ከሌሎች ዳኞች ጋር በመሰየም የዞኑን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዉሳኔ በማሻሻል ወስነዉ እያለ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ የይግባኝ ሰሚዉን ችሎት ዉሳኔ በትዕዛዝ የማጽናቱን አግባብነት ከክልሉ ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 13/2015 አንቀፅ 24(1/ሐ) ስር ከተደነገገዉ እንዲሁም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 211 እና 212 ድንጋጌዎች እና ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የእነዚህን ድንጋጌዎች አፈጻጸም አስመልክቶ በሰበር መዝገብ ቁጥር 73696 እና 185837 ከሰጠዉ የሕግ ትረጉም ጋር በማገናዘብ እንዲመረመር ተጠሪ መልስ እንዲሰጡ አዝዟል፡፡

ተጠሪ በቀን 16/09/2016ዓ/ም የተጻፈ መልስ ያቀረቡ ሲሆን በዋናዉ ጉዳይ ላይ ዉሳኔ የተሰጠዉ አመልካች የጠየቁትን ዳኝነት እና በማስረጃ የተረጋገጠዉን ፍሬ ነገር መሠረት በማድረግ በመሆኑ የተፈጸመ ስህተት የለም፡፡ከተያዘዉ ጭብጥ ጋር በተያያዘ በዳዉሮ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የተመለከቱት ዳኛ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ መዝገብ ላይ በድጋሚ ተመሳሳይ መዝገብ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ቢቀርብላቸዉ ማየት እንደሌለባቸዉ የክልሉ ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 13/2015 አንቀጽ 24(1/ሐ) ይደነግጋል፡፡ወቅቱ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተደራጀበት ወቅት ስለነበር ከፍተኛ የመዝገብ ጫና በመኖሩ ምክንያት የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ዳኛ ሳያስተዉሉ መዝገቡ ላይ ተሰይመዉ ፈርመዉ ከሆነ ጉዳዩ ለክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተመላሽ ተደርጎ ቀደም ሲል በድጋሚ ካዩ ዳኛ ዉጪ በሌሎች ዳኞች ጉዳዩ ታይቶ እንዲወሰን አመለክታለሁ በማለት መልሳቸዉን ሰጥተዋል፡፡ አመልካችም የመልስ መልሳቸዉን በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ከላይ አጠር ባለ መልኩ የተገለጸዉ የግራ ቀኙን ክርክርና በየደረጃዉ ባሉት የክልሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ውሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም ከፍ ሲል የተመለከተዉን ጭብጥ መሠረት በማድረግ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የሕግ ስህተት መፈጸም አለመፈጸሙን እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነዉም የፍትሐ ብሔር ክርክር መመራት ያለበት በልዩ ልዩ ሕግጋት በተለየ አኳኋን የተደነገጉትን ሥነ ሥርዓታዊ መርሆዎች፣ደንቦች እና በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ የተዘረጋዉን ሥርዓት በመከተል ሊሆን ይገባል፡፡ በእነዚህ በሕግጋቱ የተዘረጉትን ሥነ ሥርዓታዊ ደንቦችና መርሆዎች ሳይከተሉ ክርክሮችን መምራት እና ዉሳኔ መስጠት የዳኝነት ነጻነትን በዳኞች ላይ የሚጥለዉን ግዴታ አለመወጣት እና የዳኝነት ሥራ አመራር ኃላፊነት በአግባቡ ተግባራዊ አለማድረግ ይሆናል፤ለክርክሩ ዉጤታማ በሆነ አግባብ ጊዜ፣ገንዘብና የሰዉ ሀብት (judicial economy) በመጠቀም እልባት እንዳይሰጥ ከማድረግ አልፎ የተከራካሪ ወገኖችን ሥነ ሥርዓታዊ ፍትሕ (procedural justice) ያጓድላል ፤ እንዲሁም የተከራካሪ ወገኖችን የሥረ ነገር መብት (substantive right) እስከማሳጣት የሚያደርስ ጉዳት የሚያስከትል መሠረታዊ የሕግ ስህተት ይሆናል፡፡እነዚህን ሥነ ሥርዓታዊ መርሆዎችና ደንቦች ባለመከተል ክርክር በመምራት ዉሳኔ መስጠት መሠረታዊ የሕግ ስህተት እንደሆነ ይህ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 37391(ቅጽ 8)፣189065፣234426፣238091 እና በሌሎች መዝግብት ላይ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

ከሥነ ሥርዓታዊ ደንቦች መካከል ስለዳኞች ወይም ችሎት አሰያየም እና ዳኞች ከችሎት ስለሚነሱበት አግባብ በሚመለከት በፌዴራልና በክልል ሕግጋት የተደነገገዉ ይገኝበታል፡፡ለተያዘዉ ጉዳይ ተገቢዉን እልባት መስጠት እንዲቻል ስለዳኞች ወይም ችሎት አሰያየም እና ዳኞች ከችሎት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ስለሚነሱበት አግባብ ለዚህ ጉዳይ ተፈጻሚነት ያለዉ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ክልል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 13/2015 የደነገገዉን መመልከት ያስፈልጋል፡፡በዚህ አዋጅ አንቀጽ 18/3 ስር በክልሉ ጠቅላይ እና ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች የሚታይ ማንኛዉም ጉዳይ ሦስት ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት ታይቶ እንደሚወሰን አስገዳጅ በሆነ አግባብ ደንግጓል፡፡ እንዲሁም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 24(1/ሐ) ስር ዳኛዉ ክርክሩን አስቀድሞ በዳኝነት ተመልክቶ ከሆነ በቀጣይ ባሉት ንዑሳን አንቀጾች በተደነገገዉ አግባብ ከችሎት መነሳት እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ይህ አዋጅ የጸናዉ ከቀን 07/06/2015ዓ/ም ጀምሮ እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 40 ላይ ተመልክቷል፡፡

ይህ አዋጅ ከቀን 07/06/2015ዓ/ም ጀምሮ ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት በክልሉ ተፈጻሚ ሲሆን የነበረዉ የክልሉ ፍርድ ቤቶች ሕግ በክልሉ ምክር ቤት በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 3/2014 አንቀጽ 3 ላይ እንደተመለከተዉ የቀድሞዉ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 43/1994 እና ማሻሻያዎቹ አዋጅ ቁጥር 85/1996 እና 130/2002 ናቸዉ፡፡ በተሻሻለዉ አዋጅ ቁጥር 43/1994 አንቀጽ 15/2 ስር በጠቅላይ ፍርድ ቤት እና በከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ችሎቶች አንድ ሰብሳቢ እና ሁለት ዳኞች ሆነዉ ተሰይመዉ እንደሚዳኙ ተደንግጓል፡፡ይህ አንቀጽ በአዋጅ ቁጥር 85/1996 የተሻሻለ ቢሆንም በጠቅላይ ፍርድ ቤት የሚገኝ የይግባኝ ችሎት ሦስት ዳኞች በተሰየሙበት ያስችላል የሚለዉ በአዋጅ ቁጥር 43/1994 አንቀጽ 15/2 ስር የተደነገገዉ ጸንቶ ቀጥሏል፡፡እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 43/1994 አንቀጽ 22(1/ለ) ስር እንደተደነገገዉ ማንኛዉም ዳኛ ክርክር የተነሳበትን ጉዳይ አስቀድሞ በዳኝነት ተመልክቶ እንደሆነ በዚሁ አንቀጽ ንኡሳን አንቀጾች በተደነገገዉ መሠረት ከችሎት መነሳት ይኖርበታል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የቀረበዉ አዋጅ ቁጥር 13/2015 ከመጽናቱ በፊት በቀን 21/04/2015 ዓ/ም ሲሆን ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ በጉዳዩ ላይ የፍርድ ዉሳኔ የሰጠዉ ደግሞ በቀን 14/11/2015 ዓ/ም አዋጅ ቁጥር 13/2015 ተፈጻሚ መሆን ከጀመረ በኋላ ነዉ፡፡የይግባኝ ክርክር ሲታይ ተፈጻሚ ሲሆን በነበረዉ አዋጅም ሆነ በጉዳዩ ላይ የፍርድ ዉሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ ተፈጻሚ ሲሆን በነበረዉ አዋጅ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማንኛዉም የይግባኝ ጉዳይ መታየትና እልባት ሊያገኝ የሚገባዉ ሦስት ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት እንደሆነ በአስገዳጅነት ተደንግጓል፡፡

በሕግ ስለዳኞች አሰያየም የሚደነገግበት ወይም አንድን ጉዳይ በዳኝነት በሚያይ ችሎት የሚሰየሙ ዳኞች ቁጥር ብዛት ሦስትና ከሦስት በላይ እንዲሆን በሕግ የሚደነገግበት ዓላማ የጉዳዩን የክብደት

ደረጃ፣ ዉስብስብነት፣ጉዳዩ በተከራካሪዎችና በአጠቃላዩ ሕብረተሰብ ላይ የሚኖረዉን አዉንታዊም ሆነ አሉታዊ ፋይዳ እና የመሳሰሉትን ምክንያቶች ታሳቢ በዳረገ መልኩ በዳኞች መካከል በሚደረግ ዉይይትና በጋራም ሆነ በተናጠል ዳኞቹ በጉዳዩ ላይ በሚያደርጉት ምርምር አከራካሪዉን ፍሬ ነገር በአግባቡ በመለየት ለሚያከራክረዉ ጉዳይ ተፈጻሚነት ያለዉን ሕግ በአግባቡ በመለየትና በመተርጎም እና/ወይም ተፈጻሚ በማድረግ በአንጻራዊነት ለጉዳዮች ትክክለኛ ዉሳኔ በመስጠት ሕዝቡ በዳኝነት አካሉ ላይ የሚኖረዉን እምነት ለማሳደግ ነዉ፡፡

በሕግ በተደነገገዉ መሰረት የዳኞች ቁጥር ተሟልቶ በተሰየሙት ችሎት በቂ ዉይይት በችሎቱ ዳኞች ሳይደረግ ዉሳኔ መስጠት ባልተሟሉ ዳኞች እንደተሰጠ ዉሳኔ/ትእዛዝ የሚቆጠር በመሆኑ ሕጉ በችሎት አሰያየም ለማሳካት የፈለገዉ ዓላማ እንዳይሳካ የሚያደረግ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 212/2 መሰረት እንደ ሥነ ሥርዓት ጉድለት (irregular proceedings) ተቆጥሮ ሕጋዊ ዉጤት ሊሰጠዉ እንደማይገባ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 73696 ላይ (ቅጽ 13) እና በሰ/መ/ቁጥር 185837(ቅጽ 25) ላይ  አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ተሰጥቷል፡፡

በተጨማሪም ዳኞች የዳኝነት ሥራቸዉን በዉጤታማነት መፈጸም እንዲችሉ የዳኝነት ነጻነት እና ገለልተኝነት መርሆዎችን በከፍተኛ ጥንቃቄ እና በጥብቅ ዲስፕሊን ተግባራዊ ማድረግ ይኖርባቸዋል(የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 79(2 እና 3) ይመለከቷል)፡፡ ዳኞች ይህንን የማያደርጉ ከሆነ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 37/1 ስር የተደነገገዉ የተከራካሪ ወገኖች ሥነ ሥርዓታዊ መብት፣ በሕገ መንግሥቱ እና በሌሎች ሕግጋት ጥበቃ የተደረገላቸዉ መሠረታዊ መብቶች ከመጣስ ባለፈ የሕግ የበላይነት ይሸረሸራል፤ሕዝቡ በዳኝነት አካሉ ላይ እምነት ያጣል፡፡ እነዚህን መርሆዎች ለማስከበር በሕግ ከተዘረጉ ሥርዓቶች ዉስጥ አንዱ ዳኞች ከችሎት ስለሚነሱበት አግባብ የተዘረጋዉ ሥርዓት ነዉ፡፡ ዳኞች አስቀድሞ በዳኝነት ያዩትን ጉዳይ በዚያዉ ፍርድ ቤት በሚገኝ ችሎት ወይም በሌላ የፍርድ ቤት ደረጃ በሚገኝ ችሎት ላይ በድጋሚ በዳኝነት ተሰይመዉ የሚያዩና በጉዳዩ ላይ ዉሳኔ የሚሰጡ ከሆነ የዳኝነት ነጻነት እና ገለልተኝነት መርሆዎች መጣስ ስለሚሆን በዚህ አግባብ የተፈጸመ ስህተት እንዲታረም የሰበር አቤቱታ ሲቀርብ እንደመሠረታዊ የሕግ ስህተት በመቁጠር ሊታረም ይገባል፡፡

በያዝነዉ ጉዳይ በዳዉሮ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩ በይግባኝ ታይቶ ሲወሰን በችሎቱ ከተሰየሙት ሦስት ዳኞች መካከል በሦስተኛ ተራ ቁጥር ላይ የተሰየሙት ዳኛ ለሁለተኛ ጊዜ ጉዳዩ በይግባኝ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሲታይ በድጋሚ በተራ ቁጥር 2 ላይ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ተሰይመዉ ዉሳኔ መስጠታቸዉ ተረጋግጧል፡፡እንዲሁም አስቀድሞ እኚሁ ዳኛ በተሰየሙበት ከፍተኛ ፍርድ ቤት ላይ የወረዳዉ ፍርድ ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ የጸና ቢሆንም እኚሁ ዳኛ ለሁለተኛ ጊዜ ጉዳዩን በይግባኝ ሲያየዩ የወረዳዉ ፍርድ ቤት ዉሳኔ መሻሩን ከዉሳኔዎቹ ተገንዝበናል፡፡ይህ ሊሆን የቻለበትን ምክንያት መመርምር በዚህ መዝገብ ላይ ከቀረበዉ አቤቱታ ማዕቀፍ ዉጭ ስለሆነ አልፈነዋል፡፡

ከዚህ በላይ እንደተገለጸዉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ላይ በዳኝነት ተሰይመዉ ዉሳኔ የሰጡበት ጉዳይ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ደረጃ ዳኛ በሆኑበት በዳኝነት እንዲያዩ ሲቀርብላቸዉ ከላይ በተጠቀሰዉ ሕግ አግባብ ዳኛዋ ከችሎት መነሳት ነበረባቸዉ፡፡በዚህ መልኩ ከችሎት መነሳት እንደነበረባቸዉ በሥራ ብዛት በመዘንጋት ወይም በሌላ ምክንያት ባለማስተዋል ከችሎት ሳይነሱ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ደረጃ በድጋሚ ተሰይመዉ ዉሳኔ ሊሰጡ የሚችሉበት አጋጣሚ ሊከሰት እንደሚችል የምንገነዘበዉ ቢሆንም ይህ ስህተት እንዲታረም ሥርዓቱን ጠብቆ ክርክር ሲቀርብ ግን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 212/2 መሰረት ታይቶ መታረም ይኖርበታል፡፡

ሲጠቃለል አንድ ዳኛ በየደረጃዉ ባሉት ሁለት ፍርድ ቤቶች ተሰይመዉ በጉዳዩ ላይ ዉሳኔ የሰጡበት አግባብ ከላይ በተጠቀሱት በነባሩ ሕግም ሆነ አሁን ተፈጻሚ እየሆነ ባለዉ የክልሉ ፍርድ ቤቶች አዋጅ ላይ ስለችሎት አሰያየም እና ዳኛ ከችሎት ስለሚነሳበት አግባብ በአስገዳጅነት የተዘረጉትን ደንቦች የጣሰ ሥነ ሥርዓታዊ ጉድለት ብቻ ሳይሆን የተከራካሪ ወገኖች ሥነ ሥርዓታዊ መብት፣ በሕገ መንግሥቱ እና በሌሎች ሕግጋት ጥበቃ የተደረገላቸዉ መሠረታዊ መብቶች እንዲጣስ፣ የሕግ የበላይነት እንዲሸረሸርና ሕዝቡ በዳኝነት አካሉ ላይ እምነት እንዲያጣ የሚያደርግ ዉጤት የሚያስከትል በመሆኑ እንደመሠረታዊ የሕግ ስህተት ተቆጥሮ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አለመታረሙ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሀ እና ሸ) እና 10(1/ሐ) መሠረት ሊታረም የሚገባዉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ ብለናል፡፡በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 18197 ላይ በቀን 14/11/2015ዓ/ም የሰጠዉ የፍርድ ዉሳኔ እና የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 18556 ላይ በቀን 21/02/2016ዓ/ም

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የሰጠዉ ትእዛዝ በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 መሰረት ተሽረዋል፡፡

2. የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መዝገቡን በማንቀሳቀስ ቀደም ሲል ጉዳዩን ያላዩ ዳኞች እንዲሰየሙ በማድረግ በግራ ቀኙ መካከል ለተደረገዉ የይግባኝ ክርክር የፍርድ ዉሳኔ እንዲሰጥ በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/2 መሰረት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡

3. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ደረጃ ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ክረምት በዳኞች እረፍት ጊዜ ተሰርቶ በ8/02/17 ተነበዋል፡፡

## ትዕዛዝ

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ለግራ ቀኙም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. በዚህ መዝገብ ላይ የፍርድ አፈጻጸም እንዲታገድ የተሰጠዉ ትእዛዝ ተነስቷል፤ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ/ጋ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የመ.ቁ.254570

ጥቅምት 08/2017ዓ/ም

ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካቾች፡ 1. አቶ ወልዴ በረካ
2. ወ/ሮ ዘውዲቱ አብዛ } ጠ/አቶ ጌታቸው መዮ -ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አለም መካ - አልተጠራም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

በመዝገቡ ላይ የቀረበው ጉዳይ ባል ሁለት ሚስቶች ያሉት ሆኖ የአንደኛዋ ሚስት ጋብቻ በፍቺ ቀሪ በሆነበት ጊዜ የጋራ ንብረት ክፍፍሉ ሊከናወንበት ከሚገባው ስርዓት ጋር ተያይዞ የቀረበ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/308822 ላይ ጥቅምት 13/2016 ዓ.ም በዋለው ችሎት አመልካቾች ያቀረቡትን የይግባኝ አቤቱታ ውድቅ ያደረገበትን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

**ማስታወሻ፡** - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በፍርድ ቤቱ በተደረገ ክርክር የአሁን ተጠሪ ከሳሽ፣ 1ኛ አመልካች ተከሳሽ እና 2ኛ አመልካች ደግሞ ጣልቃ ገብ ነበሩ፡፡ የአሁን ተጠሪ ከ1ኛ አመልካች ጋር የነበራቸው ጋብቻ በፍቺ ቀሪ መሆኑን ተከትሎ የጋራ ንብረት ናቸው ያሏቸውን በአዲስ አበባ ከተማ ኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ ወረዳ 13 ክልል ውስጥ በ1ኛ አመልካች ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ በጠቅላላው 37 ክፍል ቤቶች እና ይዞታ፣ ከዚሁ ቤት ላይ የተሰበሰበ የኪራይ ገቢ፣ በ1ኛ አመልካች ስም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የተቀመጠ ገንዘብ እና የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 2-95074 አ/አ የሆነ አውቶሞቢል የቤት ተሸከርካሪ ዘርዝረው የሚስትነት ድርሻቸውን እንዲያካፍሏቸው ጠይቀዋል፡፡

1ኛ አመልካች በበኩላቸው ክስ የቀረበበትን ቤት እና ይዞታ ያፈሩት ከተጠሪ ጋር በ1979 ዓ.ም ከመጋባታቸው በፊት ከ1950 ዓ.ም ጀምሮ ጋብቻ ፈፅመው አብሯቸው ከሚኖሩት 2ኛ አመልካች ጋር በመሆኑ እና ከጋብቻ በኋላም ተጠሪ በንብረቱ ላይ ያደረጉት አስተዋጽዖ ባለመኖሩ ቤቱም ሆነ ከቤቱ የተሰበሰበ የኪራይ ገቢ እንደማይመለከታቸው፣ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በተለያዩ ሶስት ቅርንጫፎች ተጠራቅሞ ይገኛል የተባለው ገንዘብም ቤቱን በማከራየት የተገኘ በመሆኑ አይመለከታቸውም፣ የቤት አውቶሞቢሉም ከተጠሪ ጋር የተፈራ ባለመሆኑ ሊከፈሉ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የአሁን 2ኛ አመልካችም በጣልቃ ገብነት ቀርበው ተጠሪ የክፍፍል ክስ ያቀረቡባቸው ንብረቶች ከ1ኛ አመልካች ጋር ያፈሩት እና ተጠሪን የማይመለከት መሆኑን ጠቅሰው አቤቱታው ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም በቀረበው ክስ፣ መልስ እና የጣ/ገብ አቤቱታ ላይ ግራ ቀኙን በማከራከር እና ምስክሮቻቸው በመስማት እንዲሁም ከይዞታ አስተዳደር አካል ተጨማሪ የፅሁፍ ማስረጃ እንዲቀርብ እና በችሎት እንዲብራራ ካደረገ በኋላ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በውሳኔውም ክስ ከቀረበባቸው ቤቶች ውስጥ ሶስት ክፍል ቤቶች 1ኛ አመልካች እና ተጠሪ ከመጋባታቸው በፊት የነበረ ስለመሆኑ በምስክሮች የተነገረ ቢሆንም ንብረቶቹ የተፈሩት ከ1988 በኋላ ስለመሆኑ ከክፍሉ ይዞታ አስተዳደር በተሰጠ መግለጫ እና በመግለጫው ላይ በተሰጠ የባለሙያ ማብራሪያ ተረጋግጧል፣ ተጠሪ ነዋሪነታቸው ከአዲስ አበባ ውጪ ቢሆንም ከሚኖሩበት ጉራጌ ሀገር ቆሎ እና የተለያዩ ለሆቴል ሥራ የሚሆኑ ግብአቶችን በመላክ አስተዋፅዖ ሲያበረክቱ እንደነበር የተረጋገጠ በመሆኑ አስተዋጽዖ አልነበራቸውም ሊባል አይችልም፣ ይልቁንም 2ኛ አመልካች በቤቱ ከመኖራቸው ውጭ አስተዋጽዖ የነበራቸው ለመሆኑ ያልተረጋገጠ ቢሆንም ንብረቶቹ ጋብቻው ፀንቶ ባለበት ጊዜ የተፈራ በመሆኑ በባንክ የሚገኘውን ገንዘብ ጨምሮ ክርክር የተነሳባቸውን ንብረቶች እና የኪራይ ገንዘብ የግራ ቀኙ ለ3 እኩል ይካፈሉ ብሏል፡፡ አመልካቾች ይህንኑ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ነው፡፡ አመልካቾች ህዳር 5/2016 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ ተፈፀሟል ያሏቸውን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በ1ኛ አመልካች እና በተጠሪ መካከል ጋብቻ ከመፈፀሙ በፊት የተሰራ ቤት እንደነበር ከመረጋገጡ አኳያ ተጨማሪ ክፍሎች መሰራታቸው አስቀድሞ የተሰራውን ቤት የጋራ ንብረት ያደርገዋል መባሉ የቤተሰብ ህጉን መሰረት ያደረገ ስለመሆኑ፤ 1ኛ አመልካች ከ2ኛ አመልካች ጋር የቀደመ ጋብቻ ያላቸው መሆኑና ክርክር ያስነሳው ንብረት ከ2ኛ አመልካች ጋር የተፈራ ከመሆኑ አንፃር ድርሻ ክፍፍሉ ከተጠሪ እኩል ነው መባሉ የንብረት መብትን እና ይኸው ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/50489 ላይ የሰጠውን የህግ ትርጉም የተከተለ ስለመሆኑ ሊመረመር የሚገባው ሆኖ በመገኘቱ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

በዚህ መሰረት ተጠሪ ሐምሌ 11/2011 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ክርክር የተነሳበት ቤት ከ1ኛ አመልካች ጋር በጋብቻ ውስጥ በነበርንበት ወቅት የተፈራ ከመሆኑም በላይ ቀድሞ በነበሩት ቤቶች ላይ መሰረታዊ ለውጥ የተደረገ በመሆኑ ንብረቱ በጋብቻ ውስጥ የተፈራ ነው መባሉ ተገቢ ነው፡፡ አስተዋጽዖን በተመለከተም 2ኛ አመልካች በንብረቱ ላይ ያበረከቱት አስተዋፅዖ የሌለ ስለመሆኑ በአንፃሩ ተጠሪ በአይነት የተለያየ አስተዋፅዖችን ያበረክቱ እንደነበር በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠ በመሆኑ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ይደረግልን የሚል ምላሽ ሰጥቷል፡፡ አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ በማቅረብ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊሻር ይገባል በማለት ሞግተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና መሰረታዊ የክርክሩ ይዘት ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡

በመሰረቱ በፌዴራል መንግስቱም ሆነ በብሔራዊ ክልል መንግስታት የታወጁት የቤተሰብ ህግጋት እውቅና የሚሰጡት ለአንድ ጋብቻ ብቻ ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ የቤተሰብ ህግጋቱ በጋብቻ ላይ ጋብቻን እውቅና የማይሰጡ ብቻ ሳይሆን በግልፅ ክልክላ ያደረጉበት ጉዳይም ነው፡፡ ሆኖም የህጉ ክልከላ እንዳለ ሆኖ በተግባር አንድ ወንድ ከአንድ ጋብቻ በላይ መስርቶ የሚኖር በመሆኑ እና ከንብረት አኳያ ሊከተል የሚችለውን ማህበራዊ መመሰቃቀል ለማስቀረት ሲባል ታገቢዎቹ በጋብቻ ግኑኝነቱ ውስጥ ከተፈራው ንብረት እንዲካፈሉ፤ በዚሁ ሂደትም ለንብረቶቹ መፈራት የተለየ አስተዋፅዖ ያለው ተጋቢም ማስረጃን መሰረት ባደረገ መልኩ የተሻለ ድርሻ መካፈል እንዲችል በሚል በዚሁ ችሎት በመ/ቁ/45548፤ 50489 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት ላይ በተደጋጋሚ ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡

የዚህ ትርጉም መነሻ ሀሳቡ በአንድ በኩል የኋላኛዋ ተጋቢ በቀድሞ ሚስት ጥረት በተፈራው ንብረት ያለአግባብ እንዳትበለጽግ ለመከላከል፣ በሌላ በኩል ደግሞ የኋላኛም ተጋቢም ያለአግባብ መብቷን እና የጥረቷን ውጤት እንዳታጣ ሚዛናዊ የሆነ የመብት ጥብቃ ለማድረግ እንደሆነ በፍርድ ሀተታዎቹ በግልጽ ተመላክቷል፡፡ ይህንን ለማድረግ ደግሞ በቀደመው እና በኋለኛው ጋብቻ ውስጥ የተፈራውን ንብረት እና በንብረቶቹ መፈራት ውስጥ የተጋቢዎቹ የተለየ አበርክቶ ስለመኖሩ በፍሬ ነገር ደረጃ በማስረጃ ማረጋገጥ እና የጠራ አቋም መያዝ ያስፈልጋል፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ ከግራ ቀኙ ክርክር እና በማስረጃ ተረጋግጧል ከተባለው ፍሬ ነገር መገንዘብ የተቻለው 1ኛ አመልካች ከተጠሪ ጋር በ1979 ዓ.ም 2ኛ ጋብቻ ከመፈፀማቸው በፊት ሶስት ክፍል ቪላ ቤት የነበራቸው መሆኑ፣ ይኸው ቪላ ቤትም የሆቴል አገልግሎት ይሰጥ የነበረ ሲሆን ከተጠሪ ጋር የጋብቻ ግኑኝነቱ ከተጀመረ በኋላ ተጨማሪ ክፍሎች ተገንብተውለት እና የይዘት ለውጥ ተደርጎበት ወደ መኖሪያ ቤትነት የተቀየረ መሆኑን፣ ከዚህ ውጪም ሌሎች ተጨማሪ ቤቶች የተገነቡ መሆኑን፣ ተጠሪ ነዋሪነታቸው ገጠር በሚገኝ በ1ኛ አመልካች ስም በሚገኝ ይዞታ ላይ ሆኖ ከዚያው ሆነው ለሆቴሉ ስራ የሚያስፈልጉ የምግብ ግብአቶችን ይልኩ የነበረ መሆኑን ነው፡፡

በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠው ይህ ከሆነ የመብት ድርሻውም ይህንን መስመር የሚከተል ሊሆን ይገባል፡፡ በዚሁ መሰረት ሶስት ክፍል ቪላ ቤቱ 1ኛ አመልካች እና ተጠሪ የጋብቻ ግኑኝነት ከመጀመራቸው በፊት የተሰራ በመሆኑ በመርህ ደረጃ ተጠሪን የሚመለከት አይደለም፡፡ ተጠሪ በዚህ ቤት ላይ የሚኖራቸው መብት በጋብቻ ግኑኝነት ውስጥ በቤቱ ላይ ባደረጉት አስተዋጾ ልክ ይሆናል፡፡ ይኸውም በጋብቻ ግኑኝነቱ ውስጥ በቤቱ ላይ የተደረገው መሻሻል መሰረታዊ የሚባል ሆኖ ከተገኘ እኩል ድርሻ የሚኖራቸው ሲሆን የተደረገው ለውጥ ከዚህ ያነሰ ከሆነ ደግሞ ያደረጉት አስተዋጾ ብቻ በባለሙያ ተጣርቶ ሊከፈላቸው የሚገባ ነው፡፡ በዚህ መልኩ በተጠሪ የድርሻ መጠን ላይ ለመወሰን ደግሞ በቤቱ ላይ በጋብቻ ግኑኝነቱ ወቅት ተደርጓል የተባለው መሻሻል መሰረታዊ ለውጥ ሆኖ ቤቱን የጋራ የሚያደርገው መሆን ያለመሆኑ በተገቢው መንገድ ሊጣራ የሚገባው ነው፡፡

ከዚህ አኳያ የስር ፍርድ ቤት በቤቱ ላይ ተጨማሪ ክፍሎች ተገንብተው የይዘት ለውጥ ተደርጎበት ከሆቴል ወደ መኖሪያነት ተለውጧል ከማለት ባለፈ ከቤቱ መሰረታዊ ስሪት እና ይዘት አኳያ ከጋብቻ ግኑኝነቱ በፊት የነበረው እና በኋላ የተደረገው መሻሻል በባለሙያ ንጽጽር ተደርጎበት የበለጠው እጅ በጋብቻ ውስጥ የተሰራ ስለመሆኑ የጠቀሰው ነገር የለም፡፡ ይህ ደግሞ ፍርድ ቤቱ የደረሰበት ድምዳሜ በአግባቡ ያልተጣራን ፍሬ ነገር መሰረት ያደረገ መሆኑን የሚያስገነዝብ በመሆኑ በእርግጥም ሊነቀፍ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

የ1ኛ አመልካች እና የተጠሪ የጋብቻ ግኑኝነት ከተጀመረ በኋላ ተሰርተዋል የተባሉትን ተጨማሪ የሚከራዩ ክፍሎችን አስመልክቶ ቤቶቹ የሚገኙት በአዲስ አባበ ከተማ ሲሆን የተጠሪ መደበኛ መኖሪያቸው ደግሞ ገጠር የነበረ ስለመሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ እንግዲህ ከላይ እንደተመለከተው የቤተሰብ ህጉ መሰረታዊ ዓላማም ሆነ ህጉት መሰረት ተደርጎ በዚህ ችሎት የተሰጠው የህግ ትርጉም ዋና ሀሳቡ ሁለት ሚስቶች ባሉበት ትዳር የጋራ ንብረት ክፍፍል ሲደረግ አንዱ በሌላው ድካም እና ጥረት አላግባብ እንዳይበለጽግ አልያም የመብት ጥሰት እንዳይፈፀምበት ሚዛን ማስጠበቅ ነው፡፡ በዚሁ መነሻ ሀሳብ አንድ ባል ሁለት ሚቶች ያሉት ቢሆንም ሁለቱ ሚስቶች በተለያየ ቦታ በሚገኝ ንብረት ይዘው ይተዳደሩ የነበረ ከሆነ አንደኛው ሚስት ሌላ ቦታ በሚገኘው ንብረት መፈራት ላይ ከሌላኛዋ ሚስት ያልተናነሰ ሚና የነበራቸው መሆኑ ካልተረጋገጠ በቀር ሊካፈሉ የሚገባው ባፈሩት ንብረት ልክ እና ባል ከሚደርሰው ድርሻ ላይ ሊሆን የሚገባው ነው፡፡

ከዚህ አኳያ ተጠሪ ገጠር ሆነው ለሆቴል ስራ የሚሆን የምግብ ግብዓቶችን መላካቸው በአዲስ አበባ ከተማ ተገንብተዋል በተባሉት ተጨማሪ ቤቶች መፈራት ላይ ከአመልካቾች ጋር እኩል ድርሻ ነበራቸው የሚያስብ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ተጠሪ ከ1ኛ አመልካች ድርሻ ላይ ከሚካፈሉ በቀር ከአመልካቾች እኩል 1/3ኛ ድርሻ የሚካፈሉበት አግባብ የለም፡፡ በባንክ የሚገኘው ገንዘብ እና ተሽከርካሪው ምንጫቸው የሆቴል ገቢ እና ከቤቶቹ የተሰበሰበው የኪራይ ገቢ በመሆኑ እኩል ለመካፈል የተለየ አበርክቶን የሚጠይቅ ባለመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ግራ ቀኙ እኩል እንዲካፈሉ በመወሰናቸው የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በአጠቃለይ ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ**

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/102803 ላይ ሰኔ 02/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ እና ይህንኑ በማፅናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/308822 ላይ ጥቅምት 13/2016 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ ህግ ቁጥር 348/1/ እና የፌዴራል የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9/1/ለ// መሰረት ተሻሽለዋል፡፡
2. ከላይ በውሳኔ ተራ ቁጥር 1 ስር በተመለከተው አግባብ፤
    - 2.1. 1ኛ አመልካች እና ተጠሪ በ1979 ዓ.ም የጋብቻ ግኑኝነት ከመጀመራቸው በፊት የነበረ ስለመሆኑ ከተረጋገጠው ሶስት ክፍል ቪላ ቤት እና በዚሁ ቤት ላይ በጋብቻ ውስጥ ከተደረገው መሻሻል ውጪ ያሉትን ተጨማሪ ክፍሎች አስመልክቶች ቤቶቹ በተሰሩበት ወቅት ተጠሪ መደበኛ ነዋሪነታቸው በገጠር የነበረ እና በቤቶቹ መፈራት ላይ ቀጥተኛ አበርክቶ የነበራቸው ስለመሆኑ ያልተረጋገጠ በመሆኑ ንብረቶቹ የአመልካቾች ሆኖ ተጠሪ ከ1ኛ አመልካች ግማሽ ድርሻ ላይ ብቻ እኩል እንዲካፈሉ ተወስኗል፡፡

2.2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በውሳኔ የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳስ ሶስት ክፍል ቪላ ቤቱን አስመልክቶ 1ኛ አመልካች እና ተጠሪ የጋብቻ ግኑኙነት ከጀመሩ በኋላ በቤቱ ላይ ተደርጓል የተባለው መሻሻል ቤቱን የጋራ ሊያደርገው የሚችል መሆን አለመሆኑን በተገቢው ማስረጃ ካጣራ በኋላ የተደረገው መሻሻል መሰረታዊ ሆኖ ቤቱን የጋራ የሚያደርገው ከሆነ ግራ ቀኙ ለሶስት እኩል እንዲካፈሉ፤ መሻሻሉ ከዚህ ውጭ ከሆነ ተጠሪ ከ1ኛ አመልካች ድርሻ ላይ ብቻ እኩል እንዲካፈሉ እንዲወስን ጉዳዩን መልሰንለታል፡፡

2.3. ከላይ በውሳኔ ተራ ቁጥር 2 ስር ከተደረገው መሻሸል ውጭ የተቀረው የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ አልተነካም፡፡

**ትዕዛዝ**

1. የዚህን ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ ካለ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ.ጥር 254909

ጥቅምት 07/ቀን 201፮ ዓ/ም

ዳኞች፡-እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች፡- ወ/ሮ ነጃት የሱፍ -አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. አቶ አራጋው ካሳው
2ኛ. አቶ አስቻለው ሃሳቡ } አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ በዳኞች የእረፍት ጊዜ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች በ05/03/2016 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የደሴ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 28705 በቀን 27/07/2014 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 55278 በቀን 14/11/2014 ዓ.ም በከፊል

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

ከሻሻለው በኋላ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 0336346 በቀን 16/02/2015 ዓ.ም አሻሽሎ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለታቸው ሲሆን በስር ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ከሳሽ ሆነው 1ኛ ተጠሪ ተከሳሽ በሆኑበት የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍል ክስ 2ኛ ተጠሪ ጣልቃ ገብ ሆነው ሆነው የቤት ሽያጭን በተመለከተ ጉዳይ ተከራክረዋል፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤት በቀን 05/04/2013 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ ከተጠሪ ጋር ከ1999 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2009 ዓ.ም ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደ ባልና ሚስት ሆነው ከሃምሌ 10 ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ ጋብቻ ፈጽመው ሲኖሩ የነበረ መሆኑን፤ በደሴ ከተማ የሚገኝ አዋሳኙ በክሳቸው የተጠቀሰ በተጠሪ ስም የተመዘገበ ግምቱ ብር 2,500,000.00 (ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ.ህ) የሆነ ሰርቪስ ያለው ቤት፣ በባንክ ውስጥ በተጠሪ ስም በተከፈተ  ሂሳብ የተቀመጠ ገንዘብ እንዲሁም የተለያዩ ተንቀሳቃሽ ንብረቶች ያላቸው መሆኑን፣ ሆኖም ተጠሪ ቤቱን ያለ አመልካች እውቅና ሽጦ የስመ ንብረት ዝውውር ሊያደርግ በሂደት ላይ እያለ አመልካች ባቀረቡት ተቃውሞ ሽያጩ ሊቆም መቻሉን ገልጸው ጋብቻው ፈርሶ ተጠሪ እነዚህን የጋራ ንብረቶች እንዲያካፍላቸውና የግላቸው የሆኑ ንብረቶችን እንዲመልስላቸው ጠይቀዋል፡፡

1ኛ ተጠሪም በቀን 25/05/2013 ዓ.ም ጽፈው  ባቀረቡት መልስ እንደ ባልና ሚስት አብረን ኖረናል የምትለው በሀሰት የቀረበ ነው፡፡ ቤቱ የተሸጠ መሆኑን አመልካች ገልጻ ባለበት የሽያጭ ውል ይፍረስልኝ ብላ መጠየቅ ሲገባት ከባልና ሚስት ንብረት ጋር ቀላቅላ ማቅረቧ ተገቢነት የለውም፡፡ ክስ የቀረበበትን ቤት 1ኛ ተጠሪ ከጋብቻ በፊት የሰራሁት ነው፡፡ ከጋብቻ በኋላ የተሰራው የፊኒሽንግ ስራ ነው፡፡ አመልካች ለቤቱ መሰራት ያበረከተችው አስተዋጽኦ የለም፡፡ ሰርቢስ ቤቱን የሰራሁት የግል ቤቴን አስይዤ በተበደርኩት ገንዘብ በመሆኑ አመልካች ልትጠይቅ አይገባም፡፡ አመልካች ባያያዘችው የባንክ ስቴትመንት የተመለከተው ገንዘብ በተጠሪ የትውልድ አካባቢ ለሚሰራ መስጊድ በተጠሪ አካውንት የሚሰበሰብ ገንዘብ በመሆኑ ልትጠይቅ አይገባም፡፡ ሌላው ገንዘብ ደግሞ የግል ቤቴን ሽጬ ገቢ የተደረገልኝ ገንዘብ በመሆኑ አመልካችን አይመለከትም፡፡ የቤት እቃዎችን ያመናቸውን እና የከዳቸውን በመዘርዘር የገለጸ ሲሆን ባቀረበው የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ደግሞ አመልካች አረብ አገር ሄዳ በደሞዟ ያገኘችው ገንዘብ የጋራ በመሆኑ ታካፍለኝ፣ ቤት ለመስራት ከኢ.ብ.ቁ.ተ የተበደርኩት ብር 70,000.00 (ሰባ ሺ.ህ) የጋራ እዳ ነው ይባልልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

አመልካችም ደሞዜን ለአመልካች እየላኩለት የነበረ በመሆኑ፣ እንዲሁም ቤት የተሠራው በዚሁ በምልከው ብር ስለሆነና ከኔ ጋር ሆኖ የተበደረው ብድር ስለሌለ ክሱ ውድቅ ይደረግ በማለት ለተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ከዚህ በኋላ 2ኛ ተጠሪ ጣልቃ በመግባት አከራካሪው ቤት ከእዳና እገዳ ነጻ መሆኑን ህጋዊነት ባለው ሰነድ አጣርቼ፣ 1ኛ ተጠሪ ሚስት የሌለው መሆኑን አረጋግጬ ገዝቸው ሰነዶቹን ተረክቤ ቤቱንም በመያዣ ውል አስይዤው እየተገለገልኩበት የምገኝ በመሆኑ አመልካችና 1ኛ ተጠሪ በዚህ ቤት ላይ መብት የላቸውም፡፡ አመልካች የቤቱ የጋራ ባለድርሻ ናት የሚባል ከሆነም የግዥ ገንዘቡን ከ1ኛ ተጠሪ ከመጠየቅ በቀር በቤቱ ላይ መብት የላትም እንዲባልልኝ እጠይቃለው የሚል ይዘት ያለው አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

አመልካች 2ኛ ተጠሪ ላቀረቡት የጣልቃ ገብ አቤቱታ መልሳቸውን ሲሰጡ 2ኛ ተጠሪ 1ኛ ተጠሪ ጋብቻ የሌለው መሆኑን ማስረጃ አይቼ አረጋገጥኩ ይበሉ እንጂ ያያዙት ማስረጃ የተሰጠው የሽያጭ ውሉ ከተፈጸመ በኋላ መሆኑ ሰነዱ ሐሰተኛ መሆኑን የሚያስረዳ ነው፡፡ ሽያጩ የተደረገው አመልካችና 1ኛ ተጠሪ በጋብቻ ውስጥ እያሉ በመሆኑና አመልካች ፈቃዱን ያልሰጠችበት በመሆኑ ውሉ ፈራሽ ሊሆን ይገባል፡፡ ውል አይፈርስም ከተባለ ቤቱ አሁን ባለው ዋጋ ተገምቶ 1ኛ ተጠሪ ለአመልካች እንዲመልስ ከቤቱ ይዞታ ውጭ የተሰራው ሰርቪስ ቤት የ1ኛ ተጠሪና አመልካች የጋራ ነው ተብሎ እኩል እንድንካፈል ይወሰንልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

1ኛ ተጠሪ በኩላቸው 2ኛ ተጠሪ ባቀረቡት አቤቱታ መሰረት ቢወሰን ቅሬታ የለኝም በማለት መልስ አቅርበዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃዎች ከመረመረ በኋላ የቀረቡት ምስክሮች አከራካሪው ቤት የተሠራው አመልካች አረብ አገር ሆና በምትልከው ብር መሆኑንና ቤቱም የአመልካችና የ1ኛ ተጠሪ የጋራ  ስለመሆኑ ያስረዱ በመሆኑ ቤቱ የጋራ ነው፡፡ በተጠሪ ስም በንግድ ባንክ ተቀማጭ ሆኖ የሚገኘው ገንዘብ ተጠሪ የግሌ ነው በማለት ቢከራከርም ማስረጃ ስላላቀረበበት ገንዘቡ የጋራ ነው፡፡ አመልካች የጠየቀችው የግል ንብረቶች ማስረጃ ስላልቀረበባቸው ተቀባይነት የላቸውም፡፡ ተጠሪ ባቀረበው የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ የጠየቀው የአመልካች ደሞዝ ቤት የተሰራበት መሆኑን ምስክሮች ያረጋገጡ በመሆኑና ቀሪ ገንዘብ ካለም ማስረጃ ስላልቀረበበት ውድቅ ተደርጓል፡፡ ከአብቁተ ተበደርኩ የሚለውም ለትዳር ጥቅም የዋለ ስለመሆኑ በማስረጃ ያልተረጋገጠ በመሆኑ ውድቅ ተደርጓል፡፡ 2ኛ ተጠሪ ያቀረቡትን አቤቱታ በተመለከተ የሽያጭ ውሉ በቀን 06/04/2012 ዓ.ም ተደርጎ 1ኛ ተጠሪ ያላገባ የሚለው ማስረጃ የተሰጠው በቀን 30/04/2012 ዓ.ም የሽያጭ ውሉ ከተደረገ በኋላ በመሆኑ ማስረጃው ተቀባይነት የሌለው በመሆኑና የአመልካች ፈቃድ ሳይጠየቅ በተደረገ የቤት ሽያጭ ውል የአመልካችና የተጠሪ የጋራ ሃብት የሆነውን ቤት የገዙ በመሆኑ ሽያጩ ህገ ወጥ በመሆኑ ፈራሽ ተደርጓል በማለት ወስኗል፡፡

2ኛ ተጠሪም በዚህ ውሳኔ ቅሬታ አድሮብኛል በማለት ለደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍ/ቤት የሽያጭ ውሉን ፈራሽ ካደረገ በኋላ ተዋዋዩቹ በተቻለ መጠን ወደ ነበሩበት መመለስ እየነበረበት በዝምታ ማለፉ ተገቢ ባለመሆኑ 1ኛ ተጠሪ ከ2ኛ ተጠሪ የተቀበሉትን የዚሁን ቤት የሽያጭ ዋጋ ብር 1,310,000.00 (አንድ ሚሊዮን ሶስት መቶ አስር ሺህ) ለ2ኛ ተጠሪ ሊመልሱ ይገባል በማለት የስር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል ቀሪውን የውሳኔ ክፍል በማጽናት ወስኗል፡፡

2ኛ ተጠሪ እና አመልካች በተለያዩ መዝገቦች ይህ ውሳኔ ስህተት አለበት በማለት የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ችሎቱም መዝገቦቹን አጣምሮ ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍ/ቤት የሽያጭ ውሉን ለማፍረስ ምክንያት ካደረጋቸው ነገሮች ውስጥ ቀዳሚው የአመልካች ፈቃድ የለም በሚል ቢሆንም ካርታው በ1ኛ ተጠሪ ስም የተመዘገበ ከመሆኑ አኳያ እና ተጠሪ ትዳር የሌለው ስለመሆኑ ክፍለ ከተማው አጣርቶ ያዋዋላቸው ከመሆኑ አኳያ በ2ኛ ተጠሪ ላይ ቸልተኝነት የሌለ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት የአመልካች ፈቃድ አለመኖር መሰረት አድርጎ ውሉን ማፍረሱ ተቀባይነት የሌለው ሲሆን ሌላው ምክንያት ደግሞ 1ኛ ተጠሪ ሽያጩ ከተፈጸመ ከ15 ቀን በኋላ የተሰጠ ትዳር የለኝም የሚለውን ማስረጃ ማያያዛቸው ሲሆን፣ አብዛኛው የውል ክፍል ከተፈጸመና በመሰረታዊ ውሉ ላይ መካካድ ከሌለ በእንደዚህ አይነት ምክንያቶች ውልን ማፍረስ እንደማይቻል የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ. 18786 (ቅጽ 4)፣ 36887 (ቅጽ 13) እና 138386 (ቅጽ 22) ትርጉም የሠጠበት በመሆኑና ውሉን ለማፍረስ በህግ ተቀባይነት ያለው ምክንያት የቀረበ ባለመሆኑ ውሉ ፈራሽ ነው መባሉ ተገቢነት ያለው ባለመሆኑ ውሉ የጸና ነው፡፡ 1ኛ ተጠሪ የባንክ ሂሳብ ውስጥ የሚገኘው ገንዘብ ከቤት ሽያጭ ውሉ ያገኘው በመሆኑ ለአመልካች ሊያካፍላት ይገባል በማለት የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡

አመልካችም የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት በ05/03/2016 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ለዚህ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፦ አከራካሪው ቤት አመልካችና 1ኛ ተጠሪ በትዳር ውስጥ እያሉ የተፈራና የጋራ ለመሆኑ በስር ፍ/ቤት ተረጋግጦ እያለና ተጠሪዎችም ያመኑት ሆኖ እያለ እንዲሁም የተጋቢዎች የጋራ የሆነን ቤት ለመሸጥና ለመለወጥ የተጋቢዎቹ ይሁንታ የሚያስፈልግ መሆኑ በአማራ ክልል የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 79 በግልጽ ተደንግጎ ባለበት የአመልካችና የ1ኛ ተጠሪ ንብረት የሆነውን የጋራ ቤት የአመልካች ፈቃድ ሳይጠየቅ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች መሻሻጣቸው በህጉ የተደነገገውን በግልጽ የሚቃረን ሆኖ እያለ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ሽያጩ ህጋዊ ነው በማለት መወሰኑ፣ በባንክ የተቀመጠው ገንዘብ ከቤት ሽያጩ በፊት የተቀመጠ ስለመሆኑ የባንክ ስቴትመንቱ እያሳየ ገንዘቡ ከቤት ሽያጩ የተገኘ ነው ተብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት በመሆኑ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው

ውሳኔ ተሽሮ የሽያጭ ውሉ ፈርሶ ድርሻዬን እንድካፈል እንዲሁም በባንክ ያለው ገንዘብ ከቤት ሽያጭ የተገኘ ባለመሆኑ ድርሻዬን እንድካፈል ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

አቤቱታው የቀረበለት የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ለዚህ ችሎት ከመራው በኋላ ይህ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ፡- የክርክሩ መነሻ በአሁን አመልካችና 1ኛ ተጠሪ መካከል የነበረው የባልና ሚስት ንብረት ክርክር ሆኖ የአሁን 2ኛ ተጠሪ ግራ ቀኙ የጋራ ንብረት ነው በሚል የሚከራከሩበትን ንብረት ከአሁን 1ኛ ተጠሪ በህጋዊ የሽያጭ ውል የገዙት መሆኑን ጠቅሰው ወደ ክርክር በጣልቃ ገብነት በመግባት ያቀረቡት ክርክር በዚያው መዝገብ ላይ ተስተናግዶ እና የውሉ ህጋዊነት ተመርምሮ የተወሰነበት አግባብ ይኸው ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 223825 ከሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም አንጻር ሊመረመር የሚገባው በመሆኑ ተጠሪዎች መልስ ይስጡበት በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

2ኛ ተጠሪም በዚህ ትዕዛዝ መሰረት በ17/10/2016 ዓ.ም የተጻፈ መልስ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፡- 2ኛ ተጠሪ አከራካሪውን ቤት ከ1ኛ ተጠሪ ስገዛ በህጉ የሚጠየቁትን ሁሉንም መስፈርቶች አሟልቼ ማለትም 1ኛ ተጠሪ ትዳር የሌለው መሆኑ አግባብነት ካለው አካል የተጻፈ የሰነድ ማስረጃ ተሟልቶ፣ ከእዳና እገዳ ነጻ መሆኑን አረጋግጬ፣ የሽያጭ ውሉ ስልጣን ባለው አካል ፊት ቀርቦ ህጋዊነቱ ተረጋግጦና ተመዝግቦ እንዲሁም ቤቱን የገዛሁት ከምሰራበት ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጋር ተያይዞ እንደመሆኑ መጠን ባንኩ በራሱ የግዥውን ህጋዊነት አረጋግጦ በመሆኑና አብዛኛው የውል ክፍል ተፈጽሞ በመሰረታዊ ውሉ ላይ መካካድ በሌለበት ሁኔታ የተደረገ በመሆኑ ውሉ ሊፈርስ አይገባም ተብሎ መወሰኑ ተገቢ ነው፡፡ አመልካችና 1ኛ ተጠሪ የሚከራከሩበትን ቤት 2ኛ ተጠሪ የገዛሁና በቤቱ ላይ መብትና ጥቅም ያለኝ በመሆኑ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 41 (1 እስከ 3) መሰረት በክርክሩ ጣልቃ መግባቴ የክርክሩ ይዘትና አድማስ ውስጥ የሚገኝ በመሆኑና መጨረሻ ላይ የሚሰጠው ውሳኔም መብትና ጥቅሜን የሚነካ ሊሆን የሚችል በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች በዚያው መዝገብ አቤቱታየን አከራክረው መወሰናቸው ተገቢነት ያለው በመሆኑ እንዲጸና እጠይቃለው የሚል ነው፡፡

1ኛ ተጠሪም በበኩላቸው በቀን 17/10/2016 ዓ.ም የተጻፈ መልስ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም:- አከራካሪውን ቤት ከአመልካች ጋር ጋብቻ ከመፈጸሜ በፊት በ1997 ዓ.ም በተመራሁት ቦታ ላይ በግል ገንዘቤ የሰራሁት የግል ንብረቴ በመሆኑ ያለ አመልካች ፈቃድ መሸጤ ተገቢነት ያለው ነው፡፡ ሽያጩም ተገቢውን መስፈርት አሟልቶ የተደረገ በመሆኑ የአማራ ክልል ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ እንዲጸናልኝ እጠይቃለው የሚል ነው፡፡

አመልካችም በ03/11/2016 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ አቤቱታቸውን አጠናክረዋል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተነው ሲሆን እኛም ያስቀርባል ሲባል የተያዘውን ጭብጥ ከግራቀኙ ክርክር፣ በስር ፍርድ ቤት ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች እና ከተገቢው ህግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው

መርምረናል፡፡ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት  የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 79/95 በአንቀጽ 79(ሀ) የባል እና የሚስት ጋራ የሆነን የማይንቀሳቀስ ንብረት መብት ለመሸጥ፣ለመለወጥ፣ለማከራየት፣በመያዣ ወይም በዋስትና ለመስጠት ወይም በማንኛውም መንገድ ለሶስተኛ ወገን ለማስተላለፍ የባል እና ሚስት ስምምነት አስፈላጊ መሆኑን የተመለከተ ሲሆን የስምምነት አለመኖር ውጤት ደግሞ ስምምነቱን ያልሰጠው ተጋቢ ለፍርድ ቤት በሚያቀርበው የዳኝነት ጥያቄ የውል ግዴታው ሊፈርስ እንደሚችል በአንቀጽ 80(1) ተመልክቷል፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች ተጣምረው ሲታዩ የባል እና ሚስት የጋራ ንብረትን ወደ ሶስተኛ ወገን በየትኛውም መንገድ ሲተላለፍ የባል እና ሚስቱ ፍቃደኝነት እንደሚያስፈልግ እንዲሁም የአንደኛው ተጋቢ ፍቃደኝነት በሌለበት ሁኔታ ንብረቱ በሌላኛው ተጋቢ ለሶስተኛ ወገን ተላልፎ ከተገኘ ግን ግዴታው ወይም ስምምነቱ ፍርድ ቤት ቀርቦ እንዲፈርስ እስካልተደረገ ድረስ ንብረቱን ለማስተላለፍ የተደረገው ስምምነት የጸና እንደሚሆን የሚያስገነዝቡ ናቸው፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይ አከራካሪውን ቤትና ይዞታ በተመለከተ አመልካች ከሌሎች ንብረቶች ጋር በማካተት በ1ኛ ተጠሪ ላይ በጥቅሉ የንብረት የክፍፍል ጥያቄ ከማቅረባቸው ውጪ በተጠሪዎች መካከል የተደረገው የሽያጭ ውል እንዲፈርስላቸው ዳኝነት የጠየቁ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት መዝገብ አያሳይም፡፡ከላይ እንደተመለከተው አከራካሪውን ቤት በተመለከተ አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር የነበራቸው ጋብቻ  መሰረት በማድረግ 1ኛ ተጠሪ ቤቱን ያለ አመልካች እውቅና ሽጦ የስመ ንብረት ዝውውር ሊያደርግ በሂደት ላይ እያለ አመልካች ባቀረቡት ተቃውሞ ሽያጩ ሊቆም መቻሉን ገልጸው ጋብቻው ፈርሶ ተጠሪ ይህንን ቤት ጨምሮ የጋራ ንብረቶችን እንዲያካፍላቸውና የግላቸው የሆኑ ንብረቶችን እንዲመልስላቸው ከመጠየቅ ውጪ በተጠሪዎች መካከል የተደረገው ውል ከአመልካች እውቀትና ፈቃድ ውጪ የተደረገ  መሆኑን በመጥቀስ የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ ዳኝነት ባልጠየቁበት የፍቺ ውጤት የሆነውን የንብረት ክፍፍል መርምሮ ተገቢውን ፍርድ በመስጠቱ ሂደት ላይ የውሉን ህጋዊነት መርምሮ የውሉን  ውጤት ቀሪ የሚያደርግ አልያም ለውሉ ውጤትን የሚሰጥ ውሳኔ መስጠት ባልተጠየቀ ዳኝነት የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 182/1 ድንጋጌን በመተላለፍ ውሳኔ እንደመስጠት የሚቆጠር ይሆናል፡፡(በሰ/መ/ቁ.223825 እና በተመሳሳይ መዝገቦች የተሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም ይመለከቷል፡፡)

ሲጠቃለል ለክርክሩ መሰረት የሆነው ቤት ላይ የሽያጭ  ውል መኖሩ እስከተረጋገጠ ድረስ፣ይህንንም ጠቅሰው አመልካች የፍቺ ውሳኔ እንዲሰጥ እና የጋራ እና የግል ንብረት ክፍፍል ዝርዝር ባቀረቡበት አመልካች በቤቱ ላይ አለኝ የሚሉትን መብት ለመጠየቅ በመጀመሪያ ይህ ውል ስልጣን ባለው አካል ዳኝነት ተጠይቆ በግራቀኝ ተገቢው ክርክር ተደርጎበት፣ በውሉ የሕግ ውጤት ላይ ተገቢው ፍርድ ሊያርፍበት ሲገባ  የፍቺ ውጤት የሆነውን የንብረት ክርክር መርምሮ ፍርድ በመስጠቱ ሂደት የክልሉ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ፍርድ ቤቶች የውሉን ህጋዊነት መርምረው አከራካሪውን ቤት በተመለከተ የተለያየ ውጤት ያለው ውሳኔ መስጠታቸው የስር ፍርድ ቤቶች የክልሉን የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 80(1) እና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉን አንቀጽ 182(1) የሚቃረን መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መደምደሚያ ላይ መድረሳቸውን የሚያሳይ በመሆኑ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

# ውሳኔ

1.የደሴ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 28705 በቀን 27/07/2014 ዓ.ም፣ የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 55278 በቀን 14/11/2014 ዓ.ም እንዲሁም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 0336346 በቀን 16/02/2015 ዓ.ም አከራካሪውን ቤት አስመልክቶ የሰጡት የውሳኔ ክፍል በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስነስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9(1)(ለ) መሰረት ተሽረዋል፡፡ቀሪው የውሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡

2.አከራካሪውን ቤት በተመለከተ በተጠሪዎች መካከል የተደረገው የሽያጭ ውል አግባብነት እና የህግ ውጤቱ ፍቺ እና የፍቺ ውጤትን አስመልክቶ ለመመርመር በተከፈተው በስር ፍርድ ቤት መዝገብ የሚስተናገድ አይደለም ብለናል፡፡

3.ይህ ውሳኔ አከራካሪውን ቤት በተመለከተ አመልካች በቤቱ ላይ አለኝ የሚሉትን መብት ክስ አቅርበው ከማረጋገጥ የሚያግዳቸው አይደለም ብለናል፡፡

4.ግራ ቀኙ በሰበር ክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

ጉዳዩ ውሳኔ ስላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ.ቁ. 255765

ጥቅምት 06/ቀን 2017ዓ/ም

ዳኞች፡-እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች፡- ወ/ሮ አባይነሽ አበበ -ቀረቡ

ተጠሪ፡- የህጻን ዩሃንስ ሃብታሙ ቻይና ሞግዚትና አስተዳዳሪ ወ/ሮ ብርቱካን ቶሎሳ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ በዳኞች እረፍት ጊዜ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች በ27/03/2016 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 93464 በቀን 22/10/2015 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 308887 በቀን 12/02/2016 ዓ.ም ማጽናቱ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለታቸው ሲሆን በስር

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ሆነው ተጠሪም ተጠሪ ሆነው የልጅነት ውሳኔ ይሰረዝልኝ በሚል ጉዳይ ተከራክረዋል፡፡

በስር ፍ/ቤት አመልካች በቀን 19/08/2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የመቃወም አቤቱታ ሟች ልጃቸው አቶ ሃብታሙ ቻይና ታሞ አልጋ ላይ ባለበት ልጅ ካለው፣ እዳ ካለበት እና የጀመረው እቁብ ካለ እንዲነግራቸው ጠይቀውት የሌለው መሆኑን ተናግሮ ከሞተ በኋላ የተጠሪ ሞግዚት ህጻኑ የሟች ልጅ ነው በማለት ያሰጡት ውሳኔ ተገቢነት የሌለው በመሆኑ የተጠሪ እና የሟች የዘረ መል ምርመራ ተደርጎ የተሰጠው ውሳኔ እንዲሻርላቸው ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪም በቀን 18/09/2015 ዓ.ም በተጻፈ መልስ የመካድ ክስ ማቅረብ የሚችለው አባት የሆነ ሰው ብቻ በመሆኑ አመልካች ይህን ክስ ለማቅረብ መብት የላቸውም፡፡ መብት አላቸው ቢባል እንኳ ክሱ ሊቀርብ የሚገባው ህጻኑ መወለዱ ከታወቀበት ወይም መወለዱ መታወቅ ከሚገባው ቀን ጀምሮ በ180 ቀን ውስጥ ሊሆን ሲገባ አመልካች የህጻኑን መወለድ እያወቁ በዚሁ የጊዜ ገደብ ክስ ያላቀረቡ በመሆኑ ክሱ በይርጋ የሚታገድ ነው የሚል መቃወሚያ ከፍሬ ነገር ክርክር ጋር አቅርበዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 174 እና 177 የመካድ ክስ በምትክነት ሊቀርብ የሚችልበትን የዝምድና ደረጃ የሚያስቀምጥ በመሆኑና አመልካችም የሟች ልጃቸው አቶ ሃብታሙ ቻይና እናት እና ወራሽ መሆናቸውን ያረጋገጡ በመሆኑ ተጠሪ ያቀረቡት የመካድ ክስ ሊቀርብ የሚገባው በአባት ብቻ ነው የሚለው መቃወሚያ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ ተጠሪ ከአመልካች ጋር ከዚህ ቀደም በመዝገብ ቁጥር 89998 በነበራቸው ክርክር በቀን 15/11/2014 ዓ.ም ጽፈው ካቀረቡት ክስ ስለተጠሪ መወለድ ያውቁ እንደነበረ መረዳት የተቻለ ሲሆን ይህም ቢያንስ አቤቱታውን ካቀረቡበት ከቀን 15/11/2014 ዓ.ም ጀምሮ ስለልጁ መወለድ እውቀቱ የነበራቸው መሆኑን ያሳያል፡፡ በመሆኑም አሁን የመቃወም አቤቱታውን እስካቀረቡበት እስከ 10/08/2015 ዓ.ም ድረስ ያለው ቀን ሲቆጠር በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 176 (1) የተመለከተው የመካድ ክስ ማቅረቢያ የ180 ቀን የጊዜ ገደብ የተጠናቀቀ በመሆኑ የአመልካች አቤቱታ በይርጋ ሚታገድ ነው፡፡ ክሱ በይርጋ አይታገድም ቢባል እንኳ የመካድ ክስ በቀጥታ የሚቀርብ ሳይሆን ለፍ/ቤት ማስፈቀጃ ቀርቦ ሲፈቀድ የሚቀርብ በመሆኑና አመልካችም ያቀረቡት ማስፈቀጃ የሌለ በመሆኑ አመልካች ያቀረቡት ክስ ውድቅ ተደርጓል በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡

አመልካችም በዚህ ውሳኔ ቅሬታ አድሮብኛል በማለት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም ፍ/ቤቱ አቤቱታውን መርምሮ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ስህተት የለበትም በማለት አቤቱታውን ውድቅ አድርጓል፡፡

አመልካችም የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት በ27/03/2016 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ለዚህ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፦ የአመልካች ልጅ አቶ ሃብታሙ ቻይና በህይወት በነበረ ጊዜ ልጅ የሌለው መሆኑ እየታወቀ የተጠሪ ሞግዚት ልጅ ወልጄለታለሁ ማለቷ ተቀባይነት ስለሌው በስር ፍ/ቤት የዘረ መል ምርመራ እንዲደረግና እንዲጣራ ጠይቄ ምርመራው ሳይደረግ ታልፎ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ተሽሮ የህጻን ዩሃንስ ሃብታሙ እና የአቶ ሃብታሙ ቻይና የዘረ መል ምርመራ እንዲደረግ፤ በአማራጭም ህጻን ዩሃንስ ሃብታሙ የአቶ ሃብታሙ ቻይና ልጅ አይደለም ተብሎ እንዲወሰን ስል እጠይቃለው የሚል ነው፡፡

አቤቱታው የቀረበለት የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ለዚህ ችሎት ከመራው በኋላ ይህ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ፦ ተጠሪ የሟች አቶ ሃብታሙ ቻይና ልጅ ነው በሚል የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ አባትነትን እንደ መካድ ክስ ተወስዶ ስለ ተጠሪ መወለድ ከሰሙበት ቀን አንስቶ በ180 ቀን ውስጥ ስላልቀረበ አቤቱታው በይርጋ ቀሪ ነው መባሉ እንዲሁም የመካድ ክስን ለማቅረብ ፈቃድ አልቀረበም በሚል የመወሰኑን አግባብነት ከፍትሐ ብሄር ህጉ ቁጥር 358 እንዲሁም ከተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 167-179 ድንጋጌዎች ጋር አገናዝቦ ለመመርመር ተጠሪ መልስ ይስጡበት ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪም በዚህ ትዕዛዝ መሰረት በ04/11 /2016 ዓ.ም የተጻፈ መልስ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፦ እኔ የተጠሪ ሞግዚት በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በጉለሌ ምድብ ችሎት በመ. ቁ 37146 በቀን 26/09/2014 ዓ.ም የሟች አቶ ሃብታሙ ቻይና ሚስትና ለህጻን ዩሃንስ ሃብታሙ ሞግዚት መሆኔን እንዲሁም ህጻኑ የሟች ወራሽ ስለመሆኑ ውሳኔ የተሰጠበትና ውሳኔውም አቤቱታ ቀርቦበት ያልተሻረ  በመሆኑ፣ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የመናገሻ ምድብ ችሎት በኮ/መ/ቁ. 90153 ህጻን ዩሃንስ የሟች አቶ ሃብታሙ ቻይና ልጅ ነው ወይስ አይደለም የሚል ጭብጥ በመያዝ ምስክሮችን ሰምቶ በቀን 24/12/2014 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ህጻን ዩሃንስ ሃብታሙ የሟች አቶ ሃብታሙ ቻይና ልጅ ስለመሆኑ ውሳኔ የሰጠ ሲሆን አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይም ይግባኝ ጠይቀው ያስሻሩትም ሆነ የተቃወሙት ባለመሆኑ የታለፈ ጉዳይ ስለሆነ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ስህተት የለበትም ተብሎ እንዲጸና እጠይቃለው የሚል ነው፡፡

አመልካችም በቀን 21/11/2016 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ አቤቱታቸውን አጠናክረዋል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለመልኩ የተገለጸዉ የግራ ቀኙ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት የሚመለከት ሲሆን እኛም የማስቀረቢያውን ጭብጥ መሰረት በማድረግ  በውሳኔው ላይ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት

ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡በመሰረቱ በተሻሻለዉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 126 እና 130 እንደተመለከተዉ አባትነት ከሚታወቅባቸዉ ሥርዓቶች ዉስጥ አንዱ አባትነት በህግ ግምት የሚታወቅበት ስርዓት ሲሆን በአንድ ወንድ እና በአንድ ሴት በመካከል በመከከላቸዉ በህግ አግባብ በጋብቻ ወይም ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረዉ በሚኖሩበት ጊዜ ዉስጥ የተፀነሰ ወይም የተወለደ ልጅ በሚኖር ጊዜ የልጁ አባቱ የሚባለዉ በዚህ ግንኙነት ዉስጥ ከሴትዮዋ ጋር የሚኖር ሰዉ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ይህ አባትነት በሕግ ግምት የሚታወቅበት አግባብ ሊስተባበል የሚችለው ደግሞ በተሻሻለዉ የቤተሰብ በሕግ አንቀጽ 167 እስከ 179 በተዘረጋዉ ልጅን የመካድ ክስ ስርዓት ነዉ፡፡ ልጅን የመካድ ክስ ተፈጻሚነት ያለዉ በአንድ ወንድ እና በአንድ ሴት መካከል በሕግ የታወቀ ግንኙነት ሲኖር እና አባትነት በሕግ ግምት የሚሰጥ በሚሆን ጊዜ ብቻ ነዉ፡፡ ይህም በሕግ ግምት አባት ነህ የተባለ ሰዉ የመካድ ክስ በማቅረብ ለማስተባበል የሚችልበት ሥርዓት ነዉ፡፡

ከላይ እንደተመለከተው አንድ ተከራካሪ ወገን በአባት በኩል ያለን መወለድ መቃወም የምትችለው የመካድ ክስ በማቅረብ ብቻ ሊሆን ይገባል፤የመካድ ክሱም የልጁ መወለድ ከታወቀበት ወይም ሊታወቅ ከሚችልበት ቀን ጀምሮ በ180 ቀናት ካልቀረበ ክሱ ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም በሚል ክሱ የህግ ውጤት ሊያጣ የሚችለው በአንድ ወንድ እና በአንድ ሴት መካከል በህግ አግባብ በጋብቻ ወይም ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረዉ በሚኖሩበት ጊዜ ዉስጥ የተፀነሰ ወይም የተወለደ ልጅ በህግ ግምቱ መሰረት የልጁ አባት ነህ ተብሎ በህግ ግምት አባትነት የተሰጠው ሰው ሲኖር ብቻ መሆኑን ከቤተሰብ ህጉ አንቀፅ 168፤170፤174(1) እና ከተመሳሳይ ድንጋጌዎች አጠቃላይ ይዘት የምንረዳው ነው፡፡በዚህ አግባብ የግራ ቀኙን ክርክር ስንመረምረው አመልካች የተጠሪን ልጅነት የህግ ውጤት ሊያሳጡት የሚችለው የመካድ ክስ በማቅረብ ብቻ ነው፤በዚህ አግባብ የመካድ ክሱ በተገቢው የክስ ማቅረቢያ ጊዜ ስላልቀረበ ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም ሊባል የሚችለው ህፃን ዮሀንስ የተፀነሰው ወይም የተወለደው በሟች ሀብታሙ ቻይና እና ወ/ሮ ብርቱካን ቶሎሳ መካከል በህግ አግባብ በጋብቻ ወይም ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረዉ በሚኖሩበት ጊዜ ዉስጥ መሆኑን መነሻ በማድረግ ሟች ሀብታሙ ቻይና የሕፃን ዮሀንስ አባት መሆኑ በህግ ግምት የተረጋገጠ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት መናገሻ ምድብ ችሎት በመ/ቁ.90153 ነሀሴ 24 ቀን 2014 ዓም የህፃን ዮሀንስ ሞግዚትና አስተዳዳሪ ሆነው የቀረቡት የህፃኑ እናት ወ/ሮ ብርቱካን ቶሎሳ የሰጡትን የምስክርነት ቃል ብቻ መሰረት በማድረግ ህፃን ዮሀንስ የተወለደው በሟች ሀብታሙ ቻይና እና ወ/ሮ ብርቱካን ቶሎሳ መካከል በህግ አግባብ የተቋቋመው ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ጊዜ በመሆኑ ህፃን ዮሀንስ የሟች ሀብታሙ ቻይና ልጅ ነው በማለት ውሳኔ የተሰጠ ቢሆንም፤በአዲስ አበባ ከተማ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.37146 በ26/09/2014 ዓም ወ/ሮ ብርቱካን ቶሎሳ የሟች አቶ ሀብታሙ ቻይና ሚስት ነበሩ በማለት በቃለ መሃላ ተረጋግጦ የቀረበን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ውሳኔ ተሰጥቶ የነበረ ቢሆንም በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መናገሻ ችሎት በመ/ቁ.89998 አመልካችና የህፃን ዮህንስ ሞግዚት ወ/ሮ ብርቱካን ቶሎሳ ክርክር አድርገው በወ/ሮ ብርቱካን ቶሎሳ እና ሟች ሀብታሙ ቻይና መካከል በባህላዊ የጋብቻ ስርዓት አይነት የተፈፀመ ጋብቻ አለመኖሩ ተረጋግጦ በመ/ቁ.37146 በ26/09/2014 ዓም የተሰጠው የሚስትነት ማስረጃ መሰረዙና ሌላው የህግ ግምትን የሚያሰጠው ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት መኖሩ አለመረጋገጡ ከመነሻውም በህግ ግምት የተፈጠረ አባትነት አለመኖሩን እያሳየ፤አመልካችም ክሱ የመካድ ክስ መሆኑን በማመልከት ክሱን ባላቀረቡበት ሁኔታ የስር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 167 እና ተከታዮቹ አግባብ በመምራት የቤተሰብ ህጉን አንቀፅ 176 (1) በመጥቀስ ክሱ የቀረበው የመካድ ክስ ማቅረቢያ የ180 ቀን የጊዜ ገደብ የተጠናቀቀ በመሆኑ የአመልካች አቤቱታ በይርጋ ሚታገድ ነው፡፡ ክሱ በይርጋ አይታገድም ቢባል እንኳ የመካድ ክስ በቀጥታ የሚቀርብ ሳይሆን ለፍ/ቤት ማስፈቀጃ ቀርቦ ሲፈቀድ የሚቀርብ በመሆኑ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ ማድረጉ ከላይ የተመለከቱትን ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች መሰረት ያላደረገ ሆኖ ስላገኘነው ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህንን በስር ፍርድ ቤት የተፈፀመን መሰረታዊ የህግ ስህተት ሊያርም ሲገባ ማፅናቱ በሰ/መ/ቁ.153814፤205030 እና በተመሳሳይ መዝገቦች የተሰጡትን አስገዳጅ ትርጉም ባላገናዘበ መልኩ ለግራ ቀኙ ክርክር እልባት መስጠቱን ስለሚያሳይ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ውሳኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 93464 በቀን 22/10/2015 ዓ.ም የሰጠውን ብይንና ይህንን ብይን በማፅናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 308887 በቀን 12/02/2016 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስነስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9(1)(ለ) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር የክርክር ነጥቦች ላይ ግራ ቀኙን በማከራከር በህጉ አግባብ የመሰለውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስነስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9(2) መሰረት መልሰንለታል፡፡
3. ግራ ቀኙ በሰበር ክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማአያገለግልም!

ትዕዛዝ

-የስር ፍርድ ቤት መዝገቦች በመጡበት አኳኋን እንዲመለሱ ታዟል፡፡

-ጉዳዩ ውሳኔ ስላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ.255898

ጥቅምት 07 ቀን 2017ዓ.ም

ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች፡- ዘይነባ ሀሰን ተወካይ ዐ.ሕግ አቶ አብዱ ካሣ ቀርቧል

ተጠሪዎች፡- 1.ሰይድ ሀሰን

2. አብዱ ሀሰን

3. መሀመድ ሀሰን | አልቀረቡም

መዝገቡ ለፍርድ የተቀጠረ ነው፡፡ በዚሁ አግባብ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

የሠበር አቤቱታው የቀረበው አመልካች ታሕሳስ 01 ቀን 2016ዓ/ም በተጻፈ የሠበር አቤቱታ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.0338524

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ሕዳር 03 ቀን 2016ዓ/ም የሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ ውርስን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቃሉ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካች ከሳሽ፤ የአሁን ተጠሪዎች እና በዚህ የሠበር ክርክር የሌሉ ወ/ሮ መይሩ የሱፍ ደግሞ ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁን አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- ከሟች አባቴ አቶ ሀሰን ሙህዲን እና ወ/ሮ ወደረ የሱፍ ጋር የመሬት ክፍፍል ሲደረግ በ1976ዓ/ም አብሬ የተቆጠርኩበት በ022 ቀበሌ ውስጥ የሚገኝ አዋሳኙ በክሱ የተገለጸ መሬት አለን፤ አመልካች የሟች አባቴ ወራሽ ነኝ፤ ተጠሪዎች መሬቱን እያረሱ አላባውን እስከ 2014ዓ/ም ድረስ ሲሰጡኝ ከቆዩ በኋላ በ2014ዓ/ም አቋርጠውብኛል፤ ስለሆነም የውርስ ድርሻ መሬቱን እንዲያካፍሉኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ተጠሪዎች በሰጡት መልስ አመልካች የቤተሰብ አባል አይደለችም፤ የመሬት አላባ ሲሰጡኝ ቆይተዋል ያለችው ሀሰት ነው፤ መሬቱን ተከፋፍለን የያዝነው በ1985 ዓ.ም በመሆኑ ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል በፍሬነገሩ ላይም ዝርዝር መልስ ሰጥተዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት የአመልካች ክስ በ10ዓመት ይርጋ የታገደ ነው በማለት በብይን ውድቅ ያደረገው ሲሆን በዚህ ብይን ላይ ይግባኝ ተጠይቆበት ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 57442 ታሕሳስ 27 ቀን 2015ዓ/ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤት የሠጠውን ብይን በመሻር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ145 መሰረት የተጠየቀውን ማስረጃ በማስቀረብ እና ክርክር በተነሳበት የውርስ መሬት አላባ አመልካች ትጠቀም ነበር ወይስ አልነበረም፤ በአላባ ተጠቅማ ከሆነ እስከ መቼ ድረስ ትጠቀም ነበር፤ ተጠሪዎች የውርሱን መሬት የያዙት ከመቼ ጀምሮ ነው፤ የአመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ ሊሆን ይገባል ወይስ አይገባም የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ እና በማስረጃ በማጣራት የመሰለውን ብይን እንዲሰጥበት በማለት ጉዳዩን ለወረዳው ፍርድ ቤት የመለሰለት ስለመሆኑ ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ የቀረበልን የውሳኔ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

ጉዳዩ የተመለሰለት የወረዳው ፍርድ ቤትም የበላይ የሆነው ፍርድ ቤት በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት የግራቀኙን ምስክሮች ከሰማ እና ከወረዳው መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት ስለጉዳዩ ተጣርቶ እንዲቀርብለት ካደረገ በኋላ መርምሮ ተጠሪዎች የሟች አባታቸውን መሬቶች አባታቸው ከሞተ ከ1977ዓ/ም ጀምሮ ተከፋፍለው ወላጅ እናታቸውን በመያዝ እያረሱ እየተጠቀሙ እንደነበር በምስክሮች ተረጋግጧል፤ የሟችን መሬቶች እያረሱ የሚያገኙት የመሬት አላባ ለአመልካች

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

እያካፈሏት የኖሩ መሆኑን የአመልካች ምስክሮች በአሳማኝ እና በተሻለ ሁኔታ አስረድተዋል፤ የተጠሪዎች ምስክሮች አላባን በሚመለከት ለአመልካች ያካፍሏት እንደነበር የሚያውቁት ነገር እንደሌለ ገልጸዋል፤ የአመልካች ምስክሮች ሚዛን በሚደፋ መልኩ ማስረዳት የቻሉ በመሆኑ የይርጋ መቃወሚያው ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ አድርጎ በፍሬጉዳዩ ላይ የግራቀኙን ማስረጃ ሰምቶ ተጠሪዎች ሟች ሀሰን ሙሀዲን በ1976ዓ/ም በድልድል ያገኘውን መሬት ለአመልካች ድርሿዋን ያካፍሏት ሲል ወስኗል።

ተጠሪዎች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.337 መሠረት ይግባኛቸው ተሰርዟል።

ተጠሪዎች በመቀጠል ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሠበር አቤቱታ አቅርበዋል። አቤቱታው የቀረበለት ፍርድ ቤትም ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ ተጠሪዎች የሟች አባታቸውን መሬት ከ1977ዓ/ም ጀምሮ ተከፋፍለው የይዞታ ማረጋገጫ ማስረጃ አውጥተው ሲጠቀሙበት እንደነበር የተረጋገጠ ፍሬነገር ነው፤ አመልካች የ2013ዓ/ም እና 2014ዓ/ም አላባ ከልክለውኛል በሚል የጠየቀች ሲሆን ምስክሮቿ የ2013ዓ/ም እና 2014ዓ/ም አላባ አካፍለዋታል በማለት መስክረዋል፤ በክሷ የተገለጸው እና በምስክሮች የተመሰከረው እርስ በእርሱ የሚጋጭ ነው፤ ስለሆነም የማስረዳት ሸክምዋን ተወጥታለች ማለት አይቻልም፤ ስለሆነም አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1000/1 መሰረት በሶስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ባልጠየቀችበት እና ከውርስ መሬቱ አላባ እየተጠቀመች መሆኑን ባላስረዳችበት ሁኔታ ያቀረበችው ክስ በፍ/ብ/ሕ/ቁ1000(1) መሠረት በይርጋ ቀሪ ነው በማለት በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን ውሳኔ ሽሯል።

አመልካች ታሕሳስ 01 ቀን 2016ዓ/ም ጽፌው ያቀረቡት የሠበር አቤቱታ የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ሲሆን ይዘቱም፡- የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የሠጠው ስልጣኑ ባልሆነ ጉዳይ ማስረጃ መዝኖ ነው፤ ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ጭብጥ በመያዝ ውሳኔ አልሰጠም፤ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠውን ፍሬነገር ዓመተምህረትን መሰረት በማድረግ ብቻ መሻሩ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው።

የአመልካች የሠበር አቤቱታ ተመርምሮ ጉዳዩ የገጠር መሬት ውርስ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን አመልካች በመሬቱ ሲጠቀሙ የቆዩ መሆናቸውን ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን እና ሀላፊነት ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች የደረሱበትን መደምደሚያ የክልሉ ሰበር ሰሚ

ችሎት የፍሬነገር ድምዳሜውን በመለወጥ አመልካች በመሬቱ አይጠቀሙም ነበር፤ ክሱ በይርጋ የታገደ ነው በማለት መወሰኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግስት አንቀጽ 80(3)(ለ) መሰረት ለሰበር ችሎት ከተሰጠው ሥልጣን አንጻር ሕጋዊነቱን ለመመር ሲባል ተጠሪዎች ቀርበው መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪዎች ሐምሌ 08 ቀን 2016ዓ/ም የሰጡት መልስ ይዘት በአጭሩ ፡- አመልካች ወራሽነቷን በሕጉ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ አላረጋገጠችም፤ ከአመልካች ጋር በአከራካሪው መሬት በጋራ ተጠቅመን አናውቅም፤ አመልካች እና ተጠሪዎች የአባታችን ወራሽ መሆናችንን በጋራ ወይም በተናጠል አሳውጀን በጋር የውርስ ድርሻችንን አውቀን በጋራ አላባ እየተጠቀምን በጋር የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በስማችን አስመዝግበን ግብር እየገበርን የያዝነው መሬት የለም፤ ስለሆነም በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ ሊጸና ይገባል  የሚል ነው፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አላቀረቡም፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸውን ይመስላል፡፡ ይህ ችሎትም ያስቀርባል ሲባል የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከመዝገቡ ይዘት መገንዘብ እንደቻልነው አመልካች ክሳቸው ባቀረቡበት ጊዜ የ2013ዓ.ም እና 2014ዓ/ም ምርት ያልተሰጣቸው ቢሆን እንኳን ክሱን በቀን 12/11/2-14ዓ/ም ያቀረቡ ከመሆኑ አንጻር በይዞታው መጠቀም ካቆሙ ከሶስት ዓመት በኋላ ክስ አቅርበዋል የሚያስብል አይደለም፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት የወረዳው ፍርድ ቤት የበላይ ሆነው ፍርድ ቤት በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት የግራቀኙን ምስክሮች በመስማት እና ከወረዳው መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት ስለጉዳዩ ተጣርቶ እንዲቀርብለት በማድረግ ማስረጃዎቹን መርምሮ እና መዝኖ ተጠሪዎች የሚች አባታቸውን መሬቶች አባታቸው ከሞተ ከ1977ዓ/ም ጀምሮ ተከፋፍለው ወላጅ እናታቸውን በመያዝ እያረሱ እየተጠቀሙ እንደነበር፤ የሚችን መሬቶች እያረሱ የሚያገኙት የመሬት አላባ ለአመልካች ያካፍሏት እንደነበር አመልካች ባቀረበቻቸው ምስክሮች በተሻለ እና ሚዛን በሚደፋ ሁኔታ ያስረዳች መሆኑን አረጋግጦ በተጠሪዎች በኩል የቀረበውን የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ አድርጎ በፍሬጉዳዩ ላይም የግራቀኙን ማስረጃ ሰምቶ ተጠሪዎች ሚች ሀሰን ሙህዲን በ1976ዓ/ም በድልድል ያገኘውን መሬት ለአመልካች ድርሻዋን ሊያካፍሏት ይገባል ከሚል ድምዳሜ ላይ  ደርሷል፡፡ ይህም የወረዳው

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ፍርድ ቤት የፍሬነገር ድምዳሜ እና ውሳኔ ጉዳዩን በይግባኝ በተመለከተው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተቀባይነት አግኝቶ ጸንቷል፡፡

በአንጻሩ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን ውሳኔ ሲሽር የሠጠው ምክንያት ተጠሪዎች የሟች አባታቸውን መሬት ከ1977ዓ/ም ጀምሮ ተከፋፍለው የይዞታ ማረጋገጫ ማስረጃ አውጥተው ሲጠቀሙበት እንደነበር የተረጋገጠ ፍሬነገር ነው፤ አመልካች የ2013ዓ/ም እና 2014ዓ/ም አላባ ክልክለውኛል በሚል የጠየቀች ሲሆን ምስክሮቿ የ2013ዓ.ም እና 2014ዓ.ም አላባ አካፍለዋታል በማለት መስክረዋል ፤ በክሷ የተገለጸው እና በምስክሮች የተመሰከረው እርስ በእርሱ የሚጋጭ ስለሆነ የማስረዳት ሸክምዋን አልተወጣችም የሚል ነው፡፡ ይህም የሰበር ሰሚ ችሎቱ ትንታኔ በቀጥታ ማስረጃ ምዘና ውስጥ የገባ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

በመሠረቱ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግስት አንቀጽ 80/3(ለ) እና በተሻሻለው የክልሉ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር መሠረት ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ስልጣን መሰረታዊ የሆነ የህግ ስሕተት የተፈጸመበትን የመጨረሻ ውሳኔ ማረም እንጂ ፍሬነገር የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን አልተሰጠውም፡፡

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 125570 እና በሌሎችም መዛግብት በሰጠው ውሳኔ ለክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ስልጣን ሥልጣን መሰረታዊ የሆነ የህግ ሥሕተት ያለበትን በክልል ጉዳዮች ላይ የተሰጠን የመጨረሻ ውሳኔ ማረም እንጂ ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ሥልጣን እንደሌለው፤ የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በተሰጠው ስልጣን መሰረት የበታች ፍ/ቤቶች በሰጡት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ሥሕተት ካለ ማረም ከሚችል በቀር ሥልጣኑ ባላቸው የበታች ፍ/ቤቶች የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር ማጣራት እና ማስረጃን መመዘን እንደማይችል በመግለጽ በየትኛውም እርከን ላይ ለሚገኙ ፍርድ ቤቶች አስገዳጅ የሆነ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

በያዝነው ጉዳይ ፍሬ ነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን በተሰጠው የወረዳው ፍርድ ቤት አመልካች ባቀረበቻቸው ምስክሮች ከመሬቱ የሚገኘውን ምርት በጋራ ትጠቀም እንደነበር በተሻለ እና ሚዛን በሚደፋ ሁኔታ ያስረዳች ስለመሆኑ በተረጋገጠበት እና ይህም ጉዳዩን በይግባኝ በተመለከተው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተቀባይነት ባገኘበት ሁኔታ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከተሰጠው ስልጣን ውጪ በመውጣት ማስረጃን መዝኖ በስር ፍርድ ቤቶች

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የተሰጠውን ውሳኔ በመሻር የሰጠው ውሳኔ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 125570 እና በሌሎችም መዛግብት ላይ የተሰጠውን ውሳኔ ያላገናዘበ እና መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በሌላ በኩል ግራ ቀኙን ያከራከረው ዋናውን የፍሬ ጉዳይ ክርክር በሚመለከትም በወረዳው ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ከመሆኑ አኳያ ጉዳዩን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከመመለስ ይልቅ እዚሁ መወሰን ፍትሐዊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 0338524 ሕዳር 03 ቀን 2016 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የቃሉ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 01-19355/2015 የካቲት 02 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ብይን እና መጋቢት 08 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 59849 መጋቢት 21 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ብይን ጸንቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፤
   - መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የመ.ቁ.256217

ጥቅምት 06/2017 ዓ.ም

ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

ሀብታሙ እርቅይሁን

መልካቾች፡ 1. ወ/ሮ ልደትሙላት
2. ወ/ሮ በአካል ሙላት
3. ወ/ሮ ትርሲት ሙላት
ወኪል 1ኛ አመልካች - ቀርበዋል

ተጠሪ፡ አቶ ዘሪሁን ሰይፉ - ቀርቧል

*መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡*

## ፍርድ

ጉዳዩ በፍርድ ቤት በጸደቀ የውርስ አጣሪ ሪፖርት ላይ የቀረበ የመቃወም አቤቱታን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበው የአሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/436250 ላይ ጥቅምት 13/2016 ዓ.ም በዋለው ችሎት የአሁን አመልካቾችን የሰበር አቤቱታ ውድቅ ያደረገበትን ትዕዛዝ በመቃወም ነው፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ክርክሩ የተጀመረው የአሁን አመልካቾች ከሌሎች ሶስት ወራሾች ጋር በመሆን በዚህ የሰበር ክርክር ተካፋይ ባልሆኑት ወ/ሮ መሰረት ማሞ በተባሉት የአሁን ተጠሪን ባለቤት ላይ በአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት ባቀረቡ አቤቱታ ነው፡፡ በአቤቱታቸውም ተጠሪዋ በውርስ ሊተላለፍላቸው የሚገባን የአውራሾቻቸውን ንብረት ጠቅልለው የያዙ መሆኑን ጠቅሰው ውርስ ተጣርቶ ድርሻቸው እንዲለይላቸው ጠይቀዋል፡፡ አቤቱታው የቀረበለት ፍርድ ቤትም ተጠሪዋን መልክ ካሰጣቸው በኋላ ግራ ቀኙ ውርሱን በራሳቸው አጣርተው እንዲያቀርቡ ትዕዛዝ ሰጥቶ ግራ ቀኙ ጥቅምት 21/2014 ዓ.ም ተፈራርመው ያቀረቡትን የውርስ አጣሪ ሪፖርት መርምሮ ህዳር 13/2014 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ አጽድቋል፡፡

ይህ ከሆነ በኋላ የአሁን ተጠሪ "የውርስ ሐብት ነው!" ከተባሉት ዋናቤት እና ሰባት ክፍል ሰርቪስ ቤቶች ውስጥ በስተምስራቅ በኩል የሚገኙት በ200 ካ/ሜ ላይ ይዞታ ላይ ያረፉት 5 ክፍል ሰርቪስ ቤቶች ከተጠሪዋ/ወ/ሮ መሰረት ማሞ/ ጋር ተጋብተው ሲኖሩ ያፈሯቸው እንጂ የውርስ ሀብት ባለመሆናቸው ከውርስ ሀብት ውጭ ሊደረጉ ይገባል በማለት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ ቁጥር 358 ጠቅሰው የመቃወም አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

ፍ/ቤቱም በቀረበው የመቃወም አቤቱታ ላይ የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃን ከሰማ በኋላ በሰጠው ውሳኔ ቀደም ሲል በፍርድ ቤቱ በፀደቀው የውርስ አጣሪ ሪፖርት ውስጥ የሚቾች የውርስ ሀብት ናቸው ከተባሉት ውስጥ የመቃወም አቤቱታ የቀረበባቸው ቤቶች የውርስ ሀብት ሳይሆኑ የአሁን ተጠሪ እና የባለቤቱ በመሆኑ ከውርስ ሀብቱ ሊለይ ይገባል በማለት የቀደመውን ውሳኔ አሻሽሏል፡፡

የአሁን አመልካቾች ይህንኑ በመቃወም እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታቸው የተለያየ ምክንያት እየተጠቀሰ በትዕዛዝ ውድቅ ተደርጓል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ላይ ነው፡፡ አመልካቾች ታህሳስ 08/2016 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እና ትዕዛዝ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት ያቀረቡት አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ ቁጥር 358 መሰረት የመቅረቡን አግባብነት እና የድንጋጌውን አድማስ ይኸው ችሎት ቀደም ሲል በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ ከሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም አንፃር ለመመርመር ሲባል ያስቀርባል ተብሎ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና መሰረታዊ የክርክሩ ይዘት ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፣ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ከክርክሩ አመጣጥ መገንዘብ እንደሚቻለው የአሁን ተጠሪ የመቃወም አቤቱታ ያቀረቡት በፍርድ ቤት በጸደቀ የውርስ አጣሪ ሪፖርት ላይ ነው፡፡ እርግጥ ነው ቀድሞ በተደረገው ክርክር የሙግቱ አካል ሊሆን ይችል የነበረ ሆኖ እርሱ ተካፋይ ባልሆነበት ክርክር በተሰጠው ፍርድ/ውሳኔ መብቱ የተነካ ሶስተኛ ወገን የተሰጠውን ፍርድ/ውሳኔ በመቃወም አቤቱታ ሊያቀርብ እንደሚችል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥት 358 ስር ተመልክቷል፡፡ የዚህ ድንጋጌ ይዘት እንደሚያስገነዝበው የመቃወም አቤቱታ ሊቀርብ የሚችለው በቀጥታ ሊፈፀም በሚችል ፍርድ/ውሳኔ ላይ ነው፡፡

ሆኖም የአሁን ተጠሪ የመቃወም አቤቱታውን ያቀረቡት ውርስ አጣሪ ሪፖርትን በማጽደቅ በተሰጠው ውሳኔ ላይ በመሆኑ የዚህ ዓይነቱ ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 358 መሰረት መቃወሚያ ሊቀርብበት የሚችል ስለመሆኑ መለየት ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም ይረዳ ዘንድ በቅድሚያ የውርስ ማጣራት ምንነት እና ውርስ አጣሪው የሚያቀርበው ሪፖርት ውጤት ምን እንደሆነ በአጭሩ ማየቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ በዚሁ አግባብ ውርስ ማጣራት ማለት የውርሱ ተቀባይ እነማን እንደሆኑ እና የውርስ ሀብቱ ምን እንደሆነ መወሰን፣ ለውርሱ የሚከፈሉትን ክፍያዎችን መቀበል እና ለመክፈል አስገዳጅ የሆኑ የሟች እዳዎችን መክፈል እንዲሁም ሟቹ በኑዛዜ ስጦታ ላደረገላቸው ሰዎች የሰጣቸውን ስጦታ መክፈል ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ህ/ቁጥር 944 ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የዚህ ድንጋጌ ይዘት ከፍ/ብ/ህ/ቁጥር 962 ጋር ተገናዝቦ ሲታይ የውርስ አጣሪ አንዱ እና ወነኛው ተግባር ጊዜያዊ የወራሾችን ማንነት የመወሰን/Provisional Determination of Persons entitled to succeed/ የሚያጠቃልል መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ የወራሾችን ማንንት ከመወሰን ረገድ ለውርሰ አጣሪ የተሰጠው ስልጣን ጊዜያዊ የተደረገበት ዋናው ምክንያት ወራሾችን የመወሰን ስልጣኑ በመርህ ደረጃ የህግ እና የሟቹ በመሆኑ እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

ያም ሆኖ በውርስ ማጠራት ሂደት ውስጥ አጣሪው የሚከውነው አንዱ ተግባር ግን የውርስ ተጠቃሚዎችን ማንነት እና የውርስ ሀብቱን መለየት እንዲሁም ከውርስ ንብረቱ ላይ የሚፈለገው እዳ ተከፍሎ ካለቀ ስለቀሪው የውርስ ሀብት ክፍፍል ተገቢውን የሂሳብ ስራ በመስራት የእያንዳንዱን ወራሾች የውርስ ድርሻ ማሳወቅንም ጭምር ስለመሆኑ ልብ ሊባል ይገባል፡፡ በህጉ አግባብ በፍ/ብ/ህ/ቁ/996 መሰረት ለወራሾች ሊሰጥ የሚገባው የወራሽነት የምስክር ወረቀትም በዚህ መልኩ ተጣርቶ እና ድርሻው ተለይቶ በቀረበ የውርስ ሀብት ላይ ስለመሆኑ ድንጋጌው በግልፅ ያሳያል፡፡ እናም በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 960 መሠረት ፍርድ ቤት ቀርቦ የተመዘገበ የውርስ አጣሪ ሪፖርት ውጤት ከፍ/ብ/ህ/ቁ/996 ድንጋጌ ጋር ተገናዝቦ ሲታይ ተለይቶ በተመለከተው ድርሻ ላይ ወራሽነትን የሚያረጋግጥ ማስረጃ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በእርግጥ በውርስ ማጣራት እና ማጽደቅ ሂደትም የውርስ ሀብቱን አልያም ወራሾቹን አስመልክቶ አከራካሪ ጉዳዮች ሊፈጠሩ ይችላል፡፡ በዚህ መልኩ አከራካሪ በሆነው ነጠብ ላይ ፍርድ ቤት ማስረጃን በመስማት አልያም በሌላ አኳኋን በማጣራት የሚሰጠው ውሳኔ የማስረጃ ውጤት ብቻ ይኖረዋል ማለት አይቻልም፡፡ የዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥም ፍርድ ቤቶች እንደየጉዳዩ አግባብነት እና የክርክር ባህሪ እየተመለከቱ የመቃወም አቤቱታውን ሊቀበሉ እንደሚችሉ ይኸው ችሎት በመ/ቁ/171964 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ እናም በፍርድ ቤት በፀደቀ የውርስ አጣሪ ሪፖርት ላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ ህግ ቁጥር 358 መሰረት የመቃወም አቤቱታ መቅረብ የሚችል መሆን ያለመሆኑ ጉዳይ በውርስ ማጣራት እና በማጸደቅ ሂደቱ አከራካሪ ነጥቦች የመኖር ያለመኖራቸው ጉዳይ እንዲሁም ፍርድ ቤቱ ነጥቦቹን በክርክር ጭብጥነት ይዞ ውሳኔ ያሳረፈበት መሆን ያለመሆኑ ላይ የሚመሰረት ይሆናል ማለት ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ መቃወሚያ የቀረበበት የፍርድ ቤቱ ውሳኔ ሪፖርቱን መርምሮ በማጽደቅ ላይ ብቻ የተወሰነ ከሆነ ጉዳዩ የማስረጃ ውጤት ያለው መሆኑን፣ ከዚህ አልፎ ፍርድ ቤት በአከራከሪ ነጥቦች ላይ ክርክር እና ማስረጃን ሰምቶ የወሰነ ከሆነ ደግሞ "በውሳኔው መብቴ ተነክቷል" የሚል ተቃዋሚ ወገን ሲቀርብ ጉዳዩ ተቀባይነትን ኖሮት ሊያስተናገድ ይችላል ማለት ነው፡፡

አሁን በቀረብው ጉዳይ በውርስ ማጣራት እና ማፀደቅ ሂደቱ ተካፋይ የነበሩት የአሁን አመልካቾች እና የተጠሪ ባለቤት ነበሩ፡፡ በሂደቱም ውርሱን በራሳቸው አጣርተው ያቀረቡ ከመሆኑም በላይ በወራሾች ማንነትም ሆነ በውርስ ሀብቱ ምንነት ላይ መካካድ አልነበረም፡፡ ፍርድ ቤቱም ያፀደቀው ይህንኑ ነው፡፡ ይሄ ከሆነ ደግሞ ሪፖርቱ በፍርድ ቤት መጽደቁ ከማስረጃነት የዘለለ ውጤት የሌለው በመሆኑ ከላይ በተሰጠው የህግ ትርጉም መሰረት ሪፖርቱን በማጽደቅ በተሰጠጠው ውሳኔ ላይ የመቃወም አቤቱታ ሊቀርብበት የሚችል አይደለም፡፡ ጉዳዩ ይህ ሆኖ እያለ ቀዳሚው ፍርድ ቤት በአሁን ተጠሪ የቀረበለትን የመቃወም አቤቱታ ተቀብሎ አከራክሮ መወሰኑም ሆነ በየደረጃው ያሉት የክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች ይህንኑ ማፅናታቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ውሳኔ</u>

1. በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት በአሁን ተጠሪ የቀረበለትን የመቃወም አቤቱታ ተቀብሎ በመ/ቁ/39492 ላይ መጋቢት 07/2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና ይህንኑ በማጽናት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/436350 በቀን 13/02/2016 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348 (1) እና በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9(1(ለ)) መሰረት ተሸረዋል፡፡

<u>ማስታወሻ</u>፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

2. የአሁን ተጠሪ የመቃወም አቤቱታ ያቀረቡበት ውሳኔ በውርስ አጣሪ የቀረበውን ሪፖርት በማጽደቅ ላይ ብቻ የተወሰነ እና የማስረጃነት ውጤት ብቻ የሚኖረው በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 358 መሰረት የመቃወም አቤቱታ ሊቀርብበት የሚችል አይደለም፡፡

<u>**ትዕዛዝ**</u>

1. የዚህን ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ ካለ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ. 256708

ቀን ፡- ጥቅምት 07 ቀን 2017 ዓ/ም

ዳኞች- እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች፡- አቶ መስፍን ግርማ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ፀሐይ ካሳዬ - ጠበቃ ቴሌራ ቤክሲሳ - ቀረቡ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍርድ**

ጉዳዩ ከገጠር መሬት ውርስ ጋር የቤተሰብ አባል በቋሚነት መኖር አለበት የሚለው መተርጎም ያለበትን አግባብ የሚመለከት ሲሆን የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡ ጉዳዩ የውርስ ንብረት ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በሉሜ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት በተደረገ ክርክር አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት፡- የሟች አያቱን ወ/ሮ ኮከቤ ተክሌ ውርስ ንብረት የሆኑ 10 ቀርጥ የእርሻ መሬት፣ የመኖሪያ ቤት፣ 20 እግር የባህር ዛፍ ስላላት ድርሻዬ ድርሻ ለመካፈል ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤቶች አመልካች የውርስ ድርሻ እንዲካፈሉ በመወሰኑ ምክንያት ለዚህ ችሎት የሰበር አቤቱታ ቀርቦ በመዝገብ ቁጥር 226120 ላይ ታይቶ በጊዜው በሥራ ላይ በነበረው ሕግ መሠረት የገጠር መሬት በምትክ ወራሽነት ስለማይወረስ አመልካች የሟች አያታቸው የቤተሰብ አባል መሆን አለመሆናቸው በጭብጥነት ተይዞ እንዲመረመር ጉዳዩን መልሶታል፡፡

በዚህም መሰረት የወረዳ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ምስክሮች በመስማት አመልካች ከ3 ዓመት እድሜው አንስቶ ከሟች ወ/ሮ ኮከቤ ተክሌ ዘንድ በማደግ ከብት እየጠበቀላት እና እየረዳት የቆዬ እሷም የእርሻ ይዞታ ስላላት ከአመልካች ጋር በዚሁ አብረው እየኖሩ እየተማረ የቆየ መሆኑና ወደ ዪኒቨርሲቲ ከሄደም ሟች እየረዳቸው እንደነበር የአመልካች ምስክሮች በመመስከራቸው አመልካች በጉዲፈቻ ህግ መሰፈርት ባይፈጽምም እንደልጅ ወይንም እንደቤተሰብ አባል በመሆን አብረው ኖረዋል፡፡ በኦሮሚያ ክልል ገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 130/1999 አንቀጽ 2/6/ እና እሱን ለማስፈጸም በወጣው ደንብ ቁጥር 151/2005 አንቀጽ 10/ለ/ መሠረት መሠረት አመልካች እንደ ቤተሰብ አባል በመሆኑ እና እንደወራሽ የሚቆጠር በመሆኑና አመልካች እና ተጠሪ እኩል መብት ያላቸው ሆኖ ስለተገኘ ሌሎች ንብረቶች የመኖሪያ ቤቶችና ባህር ዛፍ ጨምሮ በተጠሪ ስም የተመዘገበ የሟች ወ/ሮ ኮከቤ ተክሌ የእርሻ ይዞታ ከሆነው ውስጥ የአመልካች ድርሻ የንብረቶች ግምት የ 30 እና የ 40 ሉክ ቤቶች እንዲሁም ባህርዛፍ ብር 8500(ሰምንት ሺ አምስት መቶ) ብርና የእርሻ ይዞታ ድርሻውን 2.625 ቀርጥ ተጠሪ ለአመልካች አካፍላ ትሰጠው በማለት ወሰኗል፡፡

ተጠሪ ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቅሬታ ያቀረቡ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በመመርመር ቅሬታ የቀረበበት ውሳኔ የሚነቀፍ ሆኖ ስላልተገኘ ይግባኙን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

ተጠሪ በመቀጠል ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቅሬታ ያቀረቡ ሲሆን ችሎቱም ጉዳዩን በመመርመር በአዋጅ ቁጥር 130/1999 አንቀጽ 2(16) መሠረት የቤተሰብ አባል ማለት ከባለ ይዞታው የተወለዱ ልጆች ወይንም ሌሎች ሰዎች ሌላ ገቢ የሌላቸው እና በቋሚነት ከባለይዞታ ጋር የሚኖሩ የሚል በመሆኑ የአመልካች ምስክሮች በሰጡት የምስክርነት ቃል አመልካች ለሶስት አመት አባትና እናቱ ዘንድ ቆይቶ በኋላ ሰምንተኛ ክፍል እስከሚደርሰ ሟች አያቱ ዘንድ እንደቆየ በኋላም ወደ አማራ ክልል ለትምህርት እንደሄደ ክርክር ያስነሳውን ይዞታ ሟችና ተጠሪ በማከራየት ሟች እስከሞተችበት ድረሰ እየተጠቀሙበት መቆየታቸውን መስክረዋል፣ አመልካች ሟች ዘንድ ያደገ መሆኑን ቢናገሩም አመልካች ከዚህ መሬት ውጪ ሌላ ገቢ እንደሌለው እና እስከ መጨረሻው ሟችዋ ህይወትዋ እስከሚያልፍ ከእሷ ጋር በቋሚነት እየኖር መቆየቱን አላረጋገጠም ፣እራሱ አመልካች ለተወሰነ ዓመት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ከሚች ጋር አድጎ ወደሌላ እንደሄደ የተናገሩ በመሆኑ አመልካች ሌላ ገቢ የለውም የሚለውን መስፈርት የሚያሟላ አይደለም ፣የቤተሰብ አባል ክርክር በሚነሳበት ጊዜም በዚህ ይዞታ ሲጠቀሙበት ያለና ሌላ ገቢ የሌለው መሆኑ መረጋገጥ እንዳለበት በህጉ የተደነገገ በመሆኑ አመልካች ሚች ዘንድ ማደጉ ብቻ የቤተሰብ አባል የማያስብል በመሆኑ አመልካች የሚወርሰውም ይዞታ የለም በማለት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ሽሮታል ፡፡

አመልካች ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቅሬታ ያቀረቡ ቢሆንም ችሎቱም ጉዳዩን በመመርመር ቅሬታ የቀረበበት ውሳኔ የህግ ስህተት ስላልተገኘበት የሰበር አቤቱታውን ሰርዞታል፡፡

አመልካች ታህሳስ 18 ቀን 2016 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይህን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ሲሆን ይዘቱም፦ በስር ፍርድ ቤት ያቀረብኳቸው ምስክሮች ሚች ከ3 ዓመት ጀምሮ እንዳሳደገችኝ ፣እስከ 8 ኛ ክፍል እንዳስተማረችኝ፣በአካባቢው መሰናዶ ት/ቤት ባለመኖሩ ወደ ከተማ እንድሄድኩኝ ከዚያም ለዩንቨርስቲ ትምሕርት ወደ ወሎ ዮንቨርስቲ እንደሄድኩ ተመስክሮ እያለ አመልካች ሌላ ገቢ ፈጥሬ ከሚች ተለይቼ እንደኖርኩኝ ግንዛቤ በመውሰድ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ተገቢነት የሌለው ነው፣ተጠሪ እንድታካፍለኝ በክሴ ላይ የጠየኩት የእርሻ መሬት ብቻ ሳይሆን ባለ 30 እና ባለ 40 ሱክ በቆርቆሮ የተሰሩ ቤቶች ባህዛፎችም ሲሆን በአዋጅ ቁጥር 130/99 የተደነገገው ደግሞ ስለ ገጠር መሬት አጠቃቀም እንጂ ስለ ውርስ ንብረቶች አይደለም፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በከፍተኛ ትምህርት ምክንያት ለተወሰኑ ዓመታት ትምህርቴን እስከማጠናቅቅ ድረስ ከሚች ተለይቼ መቆየቴ እንደ ፍርድ ቤቱ ግንዛቤ የቤተሰብ አባል ከመሆኔ የሚያስቀር ነው ቢባል እንኳን በሌሎች ንብረቶች ላይ ምንም ሳይል ማለፉ አግባብ አይደለም፡፡ በመሆኑም የስር የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የሰበር ሰሚው ችሎትም የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ አመልካች ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ መነሻ አድረገን መዝገቡን እንደመረመርነው አመልካች የሚች አያቱ የቤተሰብ አባል መሆን አለመሆኑ በዚህ ችሎት እንዲጣራ ጉዳዩ ከተመለሰ በኍላ አመልካች ከአያቱ ጋር ከመሬቱ የሚገኘውን ገቢ እየተጋራ ሲኖር የነበረ መሆኑን በሥር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ ከመረጋገጡ አኳያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ወደ አማራ ክልል በመሄዱ የቤተሰብ አባልነቱ ተቋርጧል በሚል የደረሰበት መደምደሚያ አመልካች ለትምሕርት ወደ ወሎ ዩንቨርሲቲ መሄዴ የቤተሰብ አባልነቴን አያቋርጥም በማለት ያቀረቡት ክርክር ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 176339 ከሰጠው ውሳኔ አንጻር ሕጋዊነቱን ለመመርመር ፣ አመልካች ከገጠር መሬት በተጨማሪ ቤትና አትክልት ላይ የውርስ ድርሻ ከመጠየቁ አኳያ ከዚህ ንብረት ድርሻው ሳይወሰን መታለፉ ተገቢነቱን ሊመረመር የሚገባው በመሆኑ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት አዟል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ተጠሪ ሐምሌ 12 ቀን 2016 ዓ.ም የሰጡት መልስ ይዘት፡- የስር ወረዳ ፍርድ ቤት ከተሰጠዉ ጭብጥ ዉጪ ወጥቶ የተጠሪ ገለልተኛ የሆኑ ዝምድና እና ጓደኝነት የሌላቸዉ የአካባቢዉ ሰዎች ያለአድሎ አመልካች ከሟች ጋር ያላደገና የገዛ አባቱ ጋር አድጎ አባቱ አቶ ግርማ ካሳዬ ካረፉ በኋላ ከእንጀራ እናቱ የአባቱን መሬት ተካፍሎ ሞጆ ከተማ እናቱ ጋር ገብቶ እየተማረ መቆየቱን አስረድተዋል፣ የማትሪክ ዉጤት ሲመጣለት ወደ ወሎ ዩኒቨርስቲ በ 2003 ዓ.ም ከገባ በኋላም ጨርሶ ሲወጣም እዛዉ ሞጆ ገብቶ ኖረ እንጂ አንድም ቀን ሟቿ ጋር ኖሮ እንደማያውቅ መስክረዋል፣፣አመልካች የመጣው ሟች ከሞቱ በኋላ ነው፣ የወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 90426 አመልካች በሕጋዊ መንገድ ጉዲፈቻ ባይፈጸምም ዩኒቨርስቲ እስኪገባ ድረስ አብሮ የኖረ በመሆኑ እንደልጅ ይቆጠራል ብሎ የወሰነዉ ከተላከዉ ጭብጥ ዉጪ ወጥቶ የሰጠው ውሳኔ ነው፣ አመልካች የቤተሰብ አባል ካለመሆኑም በላይ 7 ቀርጥ የሚሆን በቂ ይዞታ መተዳደሪያም ያለዉ በመሆኑ እንዲሁም ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ በአከባቢም ያልነበረና በፊትም ሆነ በኋላ ከዩኒቨርስቲ ከወጣም በኋላ በሞጆ ከተማ የሚኖርና የራሱ መተዳደሪያ ያለዉ መሆኑ ተረጋግጧል እንዲሁም ቤት እና ዛፍ የሚለዉ ቤቱ የፈረሰ መሆኑና ዛፍም የተቆረጠ በመሆኑ 8500 ብር ብሎ ያቀረበዉም ተቀባይነት የሌለዉ በመሆኑ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ይግባኝ ሰሚ ችሎቱን ውሳኔ በማጽናት የሰጠው ውሳኔ ህግን መሰረት በማድረግ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡ አመልካች በሰጡት የመልስ መልስ ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ህጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

እንደመረመርነው ጉዳዩ አመልካች ባቀረቡት ዳኝነት መነሻ የተደረገ የውርስ ንብረት ክፍፍል ክርክርን የሚመለከት ነው፡ ቀደም ሲል በዚህ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 226120 ጉዳዩ ታይቶ በተሰጠው ውሳኔ አመልካች ለመውረስ የሚጠይቁት ከእናታቸው አስቀድሞ የሞቱትን ሟች አባታቸው አቶ ግርማ ካሳዮ ተክተው በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 842(3) መሠረት አያታቸው የሆኑት ወ/ሮ ኮከቤ ተክሌ ነው፣ለመውረስ ከሚጠይቁት ንብረቶች መካከል የገጠር መሬት አንዱ ሲሆን ፤ በኦሮሚያ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 ቁጥር 2(7), 2(16), 6(1) እና 9(1) እንዲሁም አዋጁን ለማስፈጸም በወጣው ደንብ ቁጥር 151/2005 ቁጥር 10 (1) እና (2) መሠረት የገጠር መሬት ይዞታን የመውረስ መብት ያላቸው የባለይዞታው ልጆች እና ሌሎች የመተዳደሪያ ገቢ የሌላቸው በቋሚነት ከባለይዞታው ጋር ከይዞታው በሚገኝ ገቢ የሚተዳደሩ ሰዎች ናቸው፣ ስለዚህ አመልካች የአያታቸው ይዞታ የነበረው የገጠር መሬት የመውረስ መብት ሊኖራቸው የሚችለው የሟች አያታቸው ወ/ሮ ኮከቤ ተክሌ የቤተሰብ አባል የሆኑ እንደሆነ ብቻ ነው፣ ተጠሪ የቤተሰብ አባል ካልሆኑ ሟች አባታቸውን ተክተው የአያታቸውን የገጠር መሬት ይዞታን የመውረስ መብት አይኖራቸውም በማለት የሥር ፍርድ ቤቶች

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አመልካች የሟች ወ/ሮ ኮከቤ ተክሌ የቤተሰብ አባል መሆን አለመሆናቸውን አጣርተው ውሳኔ እንዲሰጡበት ጉዳዩን መልሷል፡፡

ጉዳዩ ወደሥር ፍርድ ቤቶች ከተመለሰ በኂላ ዋናው የክርክር ጭብጥ አመልካች የቤተሰብ አባል መሆን አለመሆናቸውና የቤተሰብ አባል ከነበሩ የቤተሰብ አባልነቱ የተቋረጠ መሆን አለመሆኑ ነው፡፡ ክርክሩን በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሰረት መምራት እና መቆጣጠር የፍርድ ቤቱ ኃላፊነት ሲሆን በተገቢው ሁኔታ ካልተመራ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ዓላማዎች የሆኑትን እንደ አንጻራዊ እውነትን የመፈለግ፣ ሥነ-ሥርዓታዊ ፍትህ፣ ክርክርን ውጤታማ፣ ወጭና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ መምራት የመሳሰሉትን ማሳካት ስለማይቻል የተከራካሪዎችን መብት ይነካል፡፡ ክርክር የሚወሰነው በተጠየቀው ዳኝነት አግባብ እንደሆነ የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 182(2) ላይ ተመልክቷል፡፡ ፍርድ ቤቱም ከቀረበው ዳኝነት አኳያ ከግራቀኙ ክርክር በመነሳት በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 246 እና ተከታዮቹ መሠረት በተነሱት ጉዳዮች ጭብጥ መስርቶ ውሳኔ የመስጠት ኃላፊነት አለበት፡፡

በክርክር ሂደት ፍሬ ነገሮችን ማረጋገጥ የሚቻልባቸው ዘዴዎች ማስረጃ፣ በፍርድ ቤት በሚሠጥ የእምነት ቃል፣ ፍርድ ቤት በራሱ ግንዛቤ ሊወስድባቸው የሚችሉ ጉዳዮች፣ የሕግ ግምት እና የመሓላ ቃል ናቸው፤በፍትሐ ብሔር ክርክር የምንከተለው የማስረዳት ደረጃ ከሁለቱ ወገን የተሻለ ያስረዳው ማን ነው (preponderance of evidence) የሚለውን በመመርመር ነው፡፡ የማስረጃ ተገቢነት፣ የማስረጃው ተቀባይነትን ደንቦችን መከተል እና ለማስረጃው የሚሰጠውን ክብደት በመለየት የመወሰን ኃላፊነት ማስረጃ ለመስማትና ለመመዘን ኃላፊነት ያለባቸው ፍርድ ቤቶች ዋና ተግባር ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ የሥር ወረዳ ፍርድ ቤት የግራቀኙን ማስረጃ የሰማ ሲሆን አመልካች ከአያታቸው ጋር አብረው በጥገኝነት የኖሩ መሆኑን፣ ለትምሕርት ወደ ወሎ ዩንቨርሲት መሄዳቸውን በማጣራት አመልካች የሟች የቤሰተብ አባል በመሆናቸው የውርስ ንብረቱን ሊካፈሉ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ውሳኔውን ያጸና ሲሆን የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በበኩሉ አመልካች ከሟች አያታቸው ጋር ለተወሰነ ጊዜ አብረው ቢኖሩም በኂላ ወደ አማራ ክልል የሄዱና የቤተሰብ አባልነታቸው የተቋረጠ በመሆኑ መሬቱን የመውረስ መብት የላቸውም ሲል የሥር ፍርድ ቤቱን ውሳኔ ሽሯል፡፡ የክልሉ ሰበር አጣሪ ችሎት የአመልካችን ሰበር አቤቱታ ባለመቀበል ሰርዟል፡፡ ፍሬ ነገርን በማስረጃ አጣርተውና ማስረጃ መዝነው የመወሰን ሥልጣንና ኃላፊነት የተሰጣቸው የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካች የሟች የቤተሰብ አባል የነበሩ ስለመሆኑ አረጋግጠዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች የገጠር መሬቱን የመውረስ መብት የላቸውም በማለት የወሰነው ሟች ሕይወታቸው እስከሚያልፍ ድረስ በቋሚነት አብረው አልኖሩም በሚል ነው፡፡

ከክርክሩና ከሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ይዘት የተገነዘብነው አመልካች ከሟች አያታቸው ጋር አብረው ያደጉ ስለመሆኑና በኂላም ወደአማራ ክልል የሄዱት ለዩንቨርስቲ ትምሕርት ስለመሆኑ ነው፡፡ ለዩንቨርስቲ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ትምሕርት ወደሌላ ቦታ መሄድ በቋሚነት አብሮ መኖር መቋረጡን አያሳይም፣ ከአውራሻቸው ጋር በገቢ ጥገኛ መሆናቸውንም አያስቀርም፡፡ በቋሚነት አብሮ መኖር የሚለው የሕጉ አነጋገር ከዓላማው አንጻር መተርጎም እንዳለበት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 109697 /በቅጽ 18 እንደታተመ/ አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ለትምህርት በጊዜያዊነት መሄድም የቤተሰብ አባልነትን የማያቋርጥ ስለመሆኑ ሰበር ችሎቱ በመዝገብ ቁጥር 176339 ላይ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡አመልካች ለዩንቨርስቲ ትምሕርት በጊዜያዊነት መሄዳቸው የቤተሰብ አባልነታቸው አያቋርጠውም፡፡ ስለሆነም አመልካች የሟች ቤተሰብ አባል ባለመሆናቸው ንብረት የመውረስ መብት የላቸውም ሲል የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 436677 ጥቅምት 26 ቀን 2016 ዓ/ም እና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 418499 ሐምሌ 19 ቀን 2015 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1)(ሀ) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የምሥራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 72426 ግንቦት 21 ቀን 2015 ዓ/ም እና የሎሜ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 90426 ግንቦት 14 ቀን 2015ዓ/ም የሰጡት ውሳኔ ፀንቷል፡፡

3. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

<u>ማስታወሻ</u>፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መዝገብ ቁጥር - 257464

ቀን - 06/02/2017

ዳኞች - ሽመክት አሰፋ

ገበየሁ ፈለቀ

አለማየሁ ሹናራ

ተናኜ ጥላሁን

ዘውዲቱ ታደሰ

አመልካች - ወ/ሮ እየሩሳሌም ደሳለኝ - አልቀረቡም

ተጠሪዎች - 1. ሻለቃ አረጋኸኝ አሰፋ - ጠበቃ ሳሙኤል መንገሻ - ቀረቡ

2. የዲላ ከተማ ማዘጋጃ ቤት - ዐቃቤ ህግ አሸናፊ ገመዳ - ቀረቡ

መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው ለምርመራ ስለሆነ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የተጀመረው ዲላ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች ከሳሽ 2ኛ ተጠሪ ተከሳሽ፣ 1ኛ ተጠሪ ጣልቃ ገብ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የክሱ ይዘት በአጭሩ 62.50 ካሬ ሜትር የንግድ በግዥ በማግኘት ከ 1999 አ.ም እስከ 2001 አ.ም ድረስ እየተጠቀምኩበት እገኛለሁ፡፡ ቅድሚያ ለማልማት መብቴ ተጠብቆ ጂ + 2 ወለል ህንፃ ለመገንባት ፕሮፖዛል ባቀርብም ተከሳሽ ፍቃደኛ አልሆነም፡፡ ስለዚህ ቅድሚያ የማልማት መብት እንዲጠበቅልኝ የይዞታ ማረጋገጫና

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ግንባታ ፍቃድ እንዲሰጠኝ የተከማቸ ውዝፍ ግብር እዳ ለመንግስት ያልተከፈለው ተከሳሽ ባደረገው ክልከላ ምክንያት ስለሆነ ቀሪ እንዲሆን እንዲወሰን የሚል ነው፡፡ ተከሳሽ ለክሱ የሰጠው መልስ አመልካች ይዞታውን ከአቶ ዘውዴ ገ/ስላሴ በግዥ ያገኘችው መሆኑን ብትገልፅም ሻጭ ይዞታው የራሱ ስለመሆኑ የሚገልፅ ምንም አይነት የሰነድ ማስረጃ ባለማቅረቡ እስከ አሁን ድረስ ወደ አመልካች አልዞረም፡፡ ይዞታው በአራቱም መአዘን የመንግስት ቤቶች የሚያዋስኑት ሲሆን በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት የተወረሰ ነው፡፡ ለተሻለ ልማት በሊዝ ከፍተኛ ዋጋ በማቅረብ ጨረታውን ላሸነፈች ለወ/ሮ ያየሽ እምሬ አሁን ክርክር የተነሳበት ይዞታ ጨምሮ 625 ካሬ ሜትር የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ተሰጥቷል፡፡ ክርክር ያስነሳው ይዞታ አጠቃላይ ስፋት 62.5 ካሬ ሜትር በመሆኑ ራሱን ችሎ ለማልማት አይቻልም፡፡ ከሳሽ የያዘችውን 62.5 ካሬ ሜትር ይዞታ በጨረታ ላሸነፈችው ለወ/ሮ ያየሽ እምሬ እንድታስረክብ እንዲወሰን የሚል ነው፡፡ የአሁኑ 1ኛ አመልካች ጣልቃ ገብ በመሆኑ ያቀረበው መልስ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ ጨምሮ 625 ካሬ ሜትር ይዞታ በሊዝ ለወ/ሮ ያየሽ እምሬ ለባለቤቴ የተላለፈ ስለሆነ ህጋዊ የይዞታ ባለቤት ወ/ሮ ያየሽ እምሬ መሆኑን ያየሽ እምሬ እና ጣልቃ ገብ ጋብቻ ስለፈረሰ ይዞታው በክፍፍል ወቅት ለጣልቃ ገብ የደረሰ መሆኑን በመግለፅ የከሳሽ ክርክር ውድቅ እንዲደረግ ጠይቋል፡፡ የግራ ቀኙ የቃል እና የፅሁፍ ክርክር ከተጠናቀቀ በኃላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በድርድር እንዲጨርሱ ቢፈቅድም የድርድሩ ሀሳብ ለአመልካች 125 ካሬ ሜትር ቦታ ለጣልቃ ገብ 500 ካሬ ሜትር ይዞታ ላይ ካርታ እንዲሰራላቸው የቀረበው ሀሳብ ሌሎች የቀበሌ ቤት ተከራዮችና ጣልቃ ገብ ባለመስማማታቸው ድርድሩ አልተሳካም፡፡ ከጌድኦ ዞን ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ ቦታው ብቻውን ራሱን ችሎ ማልማት የማይቻል መሆኑን ደንብ ቁጥር 123/2007 እና መመሪያ ቁጥር 8/2007 ጠቅሶ መግለጫ ሰጥቷል፡፡ የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የከተማ መሬት ሊዝ ደንብ ቁጥር 123/2007 አንቀፅ 2(18) ስራ ራሱን ችሎ የማይለማ ቦታ ማለት ለንግድና ለሌሎች አገልግሎቶች ከ 100 ካሬ ሜትር በታችና ለመኖሪያ አገልግሎት ከከተማው የሽንሻኖ ስታንዳርድ በታች የሆነ ቦታ ማለት እንደሆነ ትርጉም የሰጠበት በመሆኑ ጣልቃ ገብ በሊዝ ከ 13 አመት በፊት የወሰደችው ይዞታ ከመሆኑም ሌላ 100 ካሬ ሜትር የማይሞላ ስለሆነ ራሱን ችሎ የሚለማ ባለመሆኑ አመልካች ቅድሚያ የማልማት መብት ይጠበቅልኝ በማለት ያነሳቸውን ክስ ባለመቀበል በአዋጅ ቁጥር 721/2011 አንቀፅ 26(1) ና (2) እንዲሁም አንቀፅ 27 መሰረት ምትክ ቦታ እና ካሳ የማግኘት መብት ተጠብቆለታል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ቅሬታ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርባለች፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የጌድኦ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 18916 በቀን 20/06/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት ውሳኔ ከመወሰኑ በፊት የአመልካች ይዞታ ድረስ በመውረድ እንዲለካ በማድረግ ቦታው ሲለካ 104 ካሬ ሜትር መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ ስፋት 104 ካሬ ሜትር በመሆኑ ተከሳሽ ዲላ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ለጣልቃ ገብ በሊዝ ቦታውን ከማስተላለፉ በፊት ከይገባኛል ባይ ነፃ አድርጎ መስጠት ሲገባው ነፃ ሳያደርግ የሰጠው ስህተት ስለሆነ የከሳሽ ይዞታ ስፋት 104 ካሬ ሜትር ስለሆነ ብቻውን ማልማት የሚችል በመሆኑ ከተከሳሽ ማዘጋጅ ቤት ጋር ውል በመግባት ቦታውን ከሳሽ ማልማት ትችላለች፡፡ ከሳሽ ቦታውን የማታለማ ከሆነ ተከሳሽ ምትክ ቦታና ካሳ ከፍሎ ከቦታው እንድትነሳ በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን ሽሮታል፡፡

የአሁን ተጠሪዎች በዚህ ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ቅሬታቸውን ለደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም መዝገቡን መርምሮ የከሳሽ ይዞታ መጠን 104 ካሬ ሜትር በመሆኑ ማልማት ይችላል ብሎ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ያልተጠየቀ ዳኝነት በመሆኑ ከሳሽ የጠየቀችው የይዞታ መጠን 62.50 ካሬ ሜትር ሲሆን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከ 100 ካሬ ሜትር በላይ ነው ማለቱ ከሳሽ ያልጠየቀችውን ዳኝነት መስጠቱ አግባብ ስላልሆነ ለከሳሽ የ 62.5 ካሬ ሜትር ይዞታ ምትክ ቦታ እና ካሳ በመክፈል እንዲያስለቅቅ በማለት የከፍተኛ ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሮ የዲላ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን ውሳኔ አፅንቶታል፡፡ አመልካች ሰበር ቅሬታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ብታቀርብም የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 000272 በቀን 25/04/2016 ዓ.ም በዋለው ችሎት አመልካች በስር ፍርድ ቤት የጠየቀችው ዳኝነት 62.5 ካሬ ሜትር ይዞታ ሲሆን ይህ ደግሞ በከተማው እስታንዳርድ መሰረት ማልማት የማይቻል መሆኑ ተረጋግጦ እና በይግባኝ ደረጃ ይዞታው መጠን 100 ካሬ ሜት በላይ ነው በማለት ያነሳችው ክርክር በስር ፍርድ ቤት ያልተነሳ አዲስ ክርክር እና ያልተጠየቀ ዳኝነት በመሆኑ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ አንቀፅ 182(2) እና 329(1) መሰረት ተቀባይነት የለውም፡፡ ይህ ባይሆን እንኳን አመልካች ለጌድኦ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ስታቀርብ የቅድሚያ የማልማት መብቷን የማይጠበቅ ወይም የማያከበር ከሆነ ተለዋጭ ቦታ ከንግድ ስራ ጋር ተመሳሳይ በሆነበት እንዲሰጠኝ በማለት ከጠየቀችው ዳኝነት አኳያ በአማራጭ የጠየቀችውን የምትክ ቦታና ካሳ ጥያቄ በመቀበል የሰጠው ውሳኔ አመልካች ያቀረበችውን ዳኝነት መሰረት በማድረግ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ አመልካችን የሚጠቅም እንጂ የሚጎዳ ባለመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አልተፈፀመም በማለት የጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔን አፅንቶታል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የአሁን ሰበር ቅሬታ የቀረበው ይህንን ውሳኔ ለማስለወጥ ነው። የሰበር ቅሬታውም ይዘት በአጭሩ የዲላ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክርክር የተነሳበት መሬት እስከ ቦታው ድረስ ወርዶ ሳያጣራ የሰጠው ውሳኔ ስህተት ነው። የጌድኦ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገቡን ወደ ኃላ መመለስ ሲችል ራሱ ወረዳው አጣርቶ የሰጠው ውሳኔ ስህተት ስለሆነ ተሽሮ ጉዳዩ በድጋሚ ተጣርቶ እንዲወሰን ለስር ፍርድ ቤት እንዲመለስልኝ። ክሱን ለማሻሻል ያቀረብኩት አቤቱታን ወደ ጎን በመተው የሰጠው ፍርድ ስህተት ስለሆነ የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መዝገብ በትዕዛዝ ቀርቦ ታይቶ እንዲወሰንልኝ የሚል ነው። ይህ ችሎት አመልካች ክሳቸውን ለማሻሻል ያቀረቡት ጥያቄ የስር ፍርድ ቤት ውድቅ ሲያደርግ የክሳቸው መሻሻል የደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መንግስት የሊዝ አፈፃፀም ደንብ ቁጥር 123/2007 አንቀፅ 2(18) ስር ከሚያስቀምጠው መስፈርት አንፃር ሊያስገኝላቸው የሚችል መብት ከመኖር አለመኖር አንፃር ክስ ሊያሻሽል አይገባም መባሉን ከፍ/ብ/ስ/ስ/ህ አንቀፅ 91 አላማና አተገባበር አንፃር ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 20456 በቅፅ 6፣ ሰበር መዝገብ ቁጥር 63699 በቅፅ 12 ከሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም አንፃር ለመመርመር ያስቀርባል በመባሉ 1ኛ ተጠሪ የበኩሉን መልስ በ 06/10/2016 ኢ.ም የተፃፈ 04 ገፅ አቅርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል። ፍሬ ነገሩ በአጭሩ አመልካች 2ኛ ተጠሪ በወጣው የሊዝ ጨረታ ማስታወቂያ እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ተወዳድራ አሸናፊ ሆና አግኝታለች። አመልካች በ 23/09/2010 ኢ.ም ባቀረባቸው ክስ በግልፅ ለክርክሩ መንስኤ የሆነው ይዞታ ስፋቱ 62.5 ካሬ ሜትር መሆኑን ከአዋሳኞቹ ጭምር ገልፃ ያመለከተች ሲሆን በግራ ቀኙ ተከራካሪዎች ስፋቱን በሚመለከት ክርክር ያልተነሳ በመሆኑ አመልካች በአማራጭ የጠየቀችው ዳኝነት ቅድሚያ የማልማት መብቴ የማይጠበቅ ከሆነ ተለዋጭ ቦታ ከንግድ ስራዬ ጋር ተመሳሳይ በሆነበት ቦታ እንዲሰጠኝ በማለት ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በማመልከታቸው መሰረት የተሰጠ ውሳኔ በአግባቡ ነው። አመልካች 104 ካሬ ሜትር ይዞታ ነው ብላ ያነሳቸው 2ኛ ተጠሪ በሊዝ ለ 1ኛ ተጠሪ የሸጠበት ይዞታ ጭምር ነው እንጂ የአመልካች ይዞታ መጠኑ 62.5 ካሬ ሜትር በላይ አይደለም። በመሆኑም 62.5 ካሬ ሜትር ብቻውን ሊለማ ስለማይችል የስር ፍርድ ቤት ለአመልካች ካሳ እና ምትክ ቦታ እንዲሰጣት የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ስለሆነ እንዲፀናልኝ የሚል ነው። 2ኛ ተጠሪ በ 05/10/2016 ኢ.ም በሰጠው 04 ገፅ ከ 1ኛ ተጠሪ ጋር ተመሳሳይ የሆነ መልስ አቅርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል። የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ በተገለፀው መሰረት የተጠቃለለ በመሆኑ እኛም ለሰበር ቅሬታ መነሻ የሆነውን ፍርድ የግራ ቀኙ ክርክር አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ሰበር ካስቀረበው ጭብጥ አንፃር እንደሚከተለው መርምረናል። መርምረን እንደተረዳነው ከሆነ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ከአቶ ዘውዴ ገ/ስላሴ 62.5 ካሬ ሜትር

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ይዞታ ጋር ያለውን የንግድ ቤት በግዥ ያገኙ መሆናቸውን በመግለፅ በቅድሚያ የማልማት መብት እንዲጠበቅልኝ የሚል ነው፡፡ የተጠሪዎች ክርክር በሊዝ አዋጅ መሰረት የተሻለ ልማት ለማልማት አቅም ላላቸው ለወ/ሮ ያየሽ እምሬ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ ጭምር 625 ካሬ ሜትር ይዞታ በሊዝ ጨረታ አሸናፊ በመሆናቸው ተላልፏል፡፡ የአመልካች ይዞታ ስፋት 62.5 ካሬ ሜትር በመሆኑ በከተማው ፕላን መሰረት ከእስታንዳርድ በታች በመሆኑ ብቻው ማልማት የሚቻል አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ይዞታውን ያገኙት ከአቶ ዘውዴ ገ/ስላሴ በግዥ እንደሆነ የገዙት ይዞታ መጠን 62.5 ካሬ ሜትር እንደሆነ በክስ ማመልከቻቸው ላይ ጠቅሰዋል፡፡ አመልካች በሰበር ቅሬታ ላይ የይዞታው ስፋት 104 ካሬ ሜትር እንደሆነ የሚያቀርቡት ክርክር ከጠየቁት ዳኝነት ውጪ ከመሆኑም ሌላ በስር ወረዳ ፍርድ ቤት ያልተነሳ አዲስ ክርክር ነው፡፡ አመልካች በግዥ ያገኙት ይዞታ 62.5 እንደሆነ ውላቸው ከማስረዳቱም ሌላ የአመልካች ክስም ያስረዳል፡፡ በስር ፍርድ ቤት አመልካች ክሱን ለማሻሻል ጥያቄ አቅርቦ እንደተከለከሉ በማስመሰል ያቀረቡትን ቅሬታ በተመለከተ በዲላ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቤቱታ ለማሻሻል ያመለከቱ ስለመሆኑ የሚያስረዳ አንድም ማስረጃ አልቀረበም በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ አንቀፅ 91(1) መሰረት ክሱን ማሻሻል የሚፈቀደው የክሱ መሻሻል ወይም የክርክሩ መለወጥ ነገሩን የበለጠ የሚያብራራው ወይም ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት የሚረዳ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይ አመልካች ክሱን ለማሻሻል የሚያቀርቡት ምክንያት የይዞታ መጠን ከ 62.5 ካሬ ሜትር ወደ 100 ካሬ ሜትር ከፍ ለማድረግ እንደሆነ ከክርክሩ ለመረዳት የቻልን ሲሆን የስፋቱ መጠን ለመጨመር ክሱ መሻሻል የሚፈቅድ አይደለም፡፡ ከመነሻውም ቢሆን ክስ ለማሻሻል አመልካች በየትኛው ፍርድ ጥያቄ አቅርበው እንደተከለከሉ ግልፅ አይደለም፡፡ በየትኛው ደረጃ ባለው ፍርድ ቤት አመልካች ክስ ለማሻሻል ያቀረቡት ጥያቄ ስለመኖሩ የሚያስረዳ ማስረጃ ባለመቅረቡ በዚህ ላይ አመልካች ያቀረቡት ቅሬታ አልተቀበልነውም፡፡ ሌላ አመልካች በሰበር ቅሬታ ላይ ያቀረቡት ነጥብ ስር ፍርድ ቤቶች እስከ ቦታው ድረስ ወርደው ሳያጣሩ ነው የወሰኑት ውሳኔ ስህተት ነው በሚል ነው፡፡ አመልካች የገዙት ይዞታ መጠን በውላቸው ላይም ሆነ በክስ ጭብጥ ላይ 62.5 ካሬ ሜትር መሆኑ በግልፅ ተጠቅሶ እያለ ፍርድ ቤት ወርዶ የሚያጠፋበት ምክንያት የለም፡፡ ፍርድ ቤት ወርዶ የሚያጣራው ፍትህ ለመስጠት አስቸጋሪ ሲሆን ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት ይዞታው የማን እንደሆነ ለማጣራት ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ግልፅ ነው፡፡ ቅድሚያ የማልማት መቻል አለመቻል ጉዳይ ነው፡፡ የአመልካች ይዞታ መጠን 62.5 ካሬ ሜትር ብቻ በመሆኑ በመመሪያ ቁጥር 123/2007 እና 8/2007 መሰረት ከ 100 ካሬ ሜትር

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በታች በመሆኑ ራሱን ችሎ የሚለማ አይደለም ተብሎ ተወስኗል፡፡ ከ 100 ካሬ ሜትር በታች በከተማ ፕላን መሰረት ከእስታንዳርድ በታች በመሆኑ ራሱን ችሎ ማልማት እንደማይቻል አመልካች አይክዱም፡፡ የአመልካች ክርክር ከ 100 ካሬ ሜትር በላይ ነው በማለት ይከራከራሉ አመልካች በግዥ ያገኙት ይዞታ መጠን 62.5 ካሬ ሜትር ሆኖ የጠየቁት ዳኝነትም 62.5 ካሬ ሜትር ይዞታ ቅድሚያ የማልማት መብት እንዲጠበቅላቸው እየጠየቁ በሌላ በኩል ይዞታው መጠን 62.5 ካሬ ሜትር አይደለም ከ 100 ካሬ ሜትር በላይ ነው ማለታቸው በዲላ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በክስ ጭብጥ ያልቀረበ አዲስ ክርክር ከመሆኑ ሌላ ያልተጠየቀ ዳኝነት ሆኖ አግኝተናል፡፡ የተሻሻለው የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ክልል መንግስት የከተማ መሬት ሊዝ ደንብ ቁጥር 123/2007 አንቀፅ 18 ከ 100 ካሬ ሜትር በታች ስፋት ያለው ይዞታ ራሱን ችሎ የማይለማ መሆኑን ይደነግጋል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት የጌድኦ ዞን ከተማ ልማትና ቤቶች መምሪያ የአመልካች ይዞታ 62.5 ካሬ ሜትር በከተማ ፕላን መሰረት ከእስታንዳርድ በታች በመሆኑ ራሱን ችሎ ማልማት እንደማይቻል ገልፆል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 1161/2011 አንቀፅ 7(1) ባለይዞታ በፕላን መሰረት ይዞታው ቅድሚያ የማልማት መብት የሚጠበቀው ከከተማ ማስተር ፕላን ጋር በማይጋጭ ሁኔታ ነው፡፡ የአመልካች ይዞታ መጠኑ 62.5 ካሬ ሜትር በመሆኑ ከ 100 ካሬ ሜትር በታች ስለሆነ በከተማው ማስተር ፕላን መሰረት ከእስታንዳርድ በታች በመሆኑ ራሱን ችሎ ማልማት የማይቻል ስለመሆኑ በደንብ ቁጥር 123/2007 በግልፅ ተደንግጎ የሚገኝ በመሆኑ ከዚህ አንፃር ስር የዲላ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአመልካች ይዞታ ብቻውን ማልማት የማይቻል ስለሆነ ቅድሚያ የማልማት ጥያቄ ውድቅ በማድረግ ለአመልካች በአዋጅ ቁጥር 721/2004 መሰረት ካሳ እና ምትክ ቦታ እንዲሰጣቸው የተወሰነው ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የጌድኦ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔን ሽሮ የዲላ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ ያፀናው ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም፡፡

ሲጠቃለል የአመልካች ይዞታ መጠን በከተማው ማስተር ፕላን መሰረት ከእስታንዳርድ በታች በመሆኑ ብቻውን ማልማት የማይቻል መሆኑን በመጥቀስ የዲላ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአመልካች ቅድሚያ የማልማት ዳኝነት ጥያቄ በክልሉ ደንብ ቁጥር 123/2007 አንቀፅ 18 መሰረት ውድቅ በማድረግ ምትክ ቦታና ካሳ እንዲሰጣት የሰጠው ውሳኔ ሆኖ እያለ የጌድኦ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዲላ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔን አለአግባብ የሻረውን በይግባኝ የተመለከተው የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ችሎት የጌድኦ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔን ሽሮ የዲላ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔን ያፀኑት በአግባቡ ስለሆነ አመልካች በስር ፍርድ ቤት በተሰጠው ውሳኔ መሰረት ካሳና ምትክ ቦታ በአዋጅ ቁጥር 1161/2011 አንቀፅ 11፣ 12፣ 13 በተገለፀው መሰረት እንዲሰጣቸው በመወሰኑ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም ብለናል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 78309 በቀን 15/02/2016 ኢ.ም የሰጠው ፍርድ እና የደቡብ ኢትየጵያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 000272 በቀን 25/4/2016 ኢ.ም የሰጠው ፍርድ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት በመሆኑ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስነ ስርአት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9(1)(ሀ) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ እግድ ካለ ተነስቷል፡፡
5. ከስር ፍርድ ቤት የመጣው መዝገብ በመጣበት ሁኔታ ይመለስ፡፡

## ትዕዛዝ

- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 259445

ጥቅምት 19 ቀን 2017 ዓ/ም

ኮድ - T05G

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ብርቅነሽ እሱባለው

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች፡- ወ/ሮ እቴነሽ እምቢበል

ተጠሪ/ዎች ፡- 1ኛ. አቶ ሮበን ነዳሳ

2ኛ. አቶ በሀይሉ ካሳሁን

3ኛ. አቶ እዝቄል ጣሴ

4ኛ. ወ/ሮ ሀመረ ድጉማ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ብይን ተሰጥቷል፡፡

**ብ ይ ን**

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 12912 ህዳር 13 ቀን 2016 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

**ማስታወሻ፡** - ይህ የ ሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነ ድ ለ ጥና ትና ምርምር ሥራ ወይምለ ግንዛቤ እ ን ጂ ለፍርድ አ ፈጻጸ ምዓላማአ ያ ገ ለ ግልም!

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው አመልካች በቤንች ሸኮ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት ክስ የቡና እና ቅመማ ቅመም ልማት ድርጅትን በተመለከተ ያደረጉት ውል እንዲፈርስ እና በተጠሪዎች ዕጅ የሚገኘው የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር፣ የኢንቨስትመንት ሰርተፍኬት ፤ እንዲሁም በቀበሌ በኩል የተዘጋጀ ቨርቫል እንዲመለስላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክር መርምሮ በመዝገብ ቁጥር 23376 ሀምሌ 14/2015 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ በውል ሰነዱ ላይ ሻጮች ብቻ ፈርመው ገዥዎች ያልፈረሙበት መሆኑን፤ እንዲሁም 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች የውጭ ሀገር ዜጋ መሆናቸው ስለተረጋገጠና በህጉ የመሬት ባለሃብት መሆን ስለማይችሉ ውሉ ሊፈርስ ይገባል፤ ገዥዎች ለሻጭ የከፈሉት የቀብድ አጠፌታ እና ተጨማሪ ክፍያ በጠቅላላው ብር 550,000.00 (አምስት መቶ ሃምሳ ሺህ) እንዲመለስላቸው፤ እንዲሁም የተጠየቁት ሰነዶች ለአመልካች እንዲመለሱ በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ የአሁን ተጠሪዎች ቅር ተሰኝተው ይግባኝ ለደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የይግባኝ ክርክሩን መርምሮ ከፍሲል በመግቢያችን በገለጽነው ቀን በሰጠው ውሳኔ ግራቀኙ በውላቸው ላይ ግዴታቸውን ለመወጣት ካስቀመጡት የሁለት ወር ጊዜ ገደብ አኳያ የአሁን አመልካች የሰጡት የማስጠንቀቂያ ጊዜ ተጠሪዎች ቀርበው ግዴታቸውን ለመፈፀም በቂ ባለመሆኑ ተጠሪዎች እንደውሉ ግዴታቸውን አልተወጡም ተብሎ ውሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያሳለፈውን ውሳኔ ሽሯል፡፡

የሰበር አቤቱታው ለዚህ ፍርድ ቤት የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች የካቲት 5/2016 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር ማመልከቻ ተፈፀመ የሚሉትን የህግ ስህተት በመዘርዘር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ተብሎ ተሽሮ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያሳለፈው ውሳኔ እንዲፀና ጠይቀዋል፡፡

ቅሬታው በአጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ አመልካች እና ተጠሪዎች በፈፀሙት የሽያጭ ውል መሰረት አመልካች ከ3ኛ ወገን ነፃ ካደረጉ በኃላ ተጠሪዎች ግዴታቸውን እንዲወጡ ማስጠንቀቂያ የሰጡበት ጊዜ በቂ አይደለም የመባሉን እና ውሉ ይፈፀም የሚባል ከሆነም ተጠሪዎች ከፍለው እንዲፈጽሙ ሳይደረግ የመታለፉን አግባብነት ከሰ/መ/ቁ 39568 አንጻር ለማየት በሚል ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት እንዲተላለፍ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረው በዚህ ሁኔታ ነው፡፡ በበኩላችን የሰበር አጣሪ ችሎቱ ጉዳዩን የመራበት ጭብጥ ከመታየቱ በፊት ጉዳዩ የይግባኝ ደረጃውን የጨረሰና በሰበር ለመታየት የሚችል መሆን አለመሆኑን መመርመሩ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው አመልካች የጉራፈርዳ ወረዳ ነዋሪ ሲሆኑ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች፤ እንዲሁም 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ደግሞ የውጪ ዜጎች መሆናቸው ተመልክቷል፡፡ የቤንች ሸኮ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ተቀብሎ በማከራከር የወሰነው በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 80(4) መሰረት በተሰጠው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጣምራ ስልጣን መሰረት ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በይግባኝ በማየት የወሰነውም በህገመንግስቱ አንቀፅ 80(2) በተሰጠው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሥልጣኑ ነው፡፡ ጉዳዩ በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 5(1) (ሸ) እና (በ) መሠረት የፌደራል ጉዳይ ከሆነና የቤንች ሸኮ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጣምራ ሥልጣኑ አይቶ የሰጠውን ውሣኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጣምራ ሥልጣኑ አይቶ ውሳኔውን ከለወጠው አመልካች ይግባኝ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ማቅረብ እንደሚኖርባቸው ከአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 9(4) ግልጽ ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ይሁንና አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት በቅድሚያ ጉዳዩ በይግባኝ እንዲታይና የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ሣያቀርቡና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የመጨረሻ ውሣኔ ሣይሰጥበት ነው፡፡

እንደሚታወቀው ይህ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በዳኝነት አይቶ ውሣኔ የሚሰጠው የመጨረሻ ውሣኔ ባገኙ ጉዳዮች ላይ እንደሆነ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 80(3)(ሀ) እና በፌ/ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 ስር ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም አመልካች የይግባኝ ደረጃውን ሣይጨርስ ጉዳዩ በሰበር ታይቶ እንዲወሰን ያቀረቡት አቤቱታ የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

**ት ዕ ዛ ዝ**

- አመልካች ይግባኝ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በማቅረብ ጉዳዩ የመጨረሻ ውሣኔ እንዲያገኝ ሳያደርጉ ለሰበር ችሎት ያቀረቡት አቤቱታ የሚስተናግድበት የህግ አግባብ የሌለ በመሆኑ አቤቱታው ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ም

የሰ/መ/ቁጥር---262248

ቀን- ጥቅምት 06 ቀን 2017 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ብርሃኑ መንግስቱ

ማርታ ተካ

**አመልካች**፡- ወ/ሮ መነን መላኩ - አልቀረቡም

**ተጠሪ**፡- የኦሮሚያ ጠቅላይ ዐ/ሕግ - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ጉዳዩ ወንጀል ሲሆን የተጀመረዉ ተጠሪ በሸገር ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት በአመልካች እና በአቶ ቴዎድሮስ ንጉሴ ላይ በመሠረተዉ ክስ መነሻነት ነዉ፡፡ የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ በሸገር ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 76549 ጥር 03 ቀን 2016 ዓ.ም እና ጥር 07 ቀን 2016 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት ተሰጥቶ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎት በተሰጡ ትዕዛዞች የጸናዉ የጥፋተኝነትና የቅጣት ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በሚል ነዉ፡፡

ተጠሪ በአመልካች እና በስር 2ኛ ተከሳሽ በነበሩት አቶ ቴዎድሮስ ንጉሴ ላይ ያቀረበዉ ክስ ይዘት፡- የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1/ሀ እና ለ) እና የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

501/1998 አንቀጽ 4 እና 41(1) የተመለከተዉን በመተላለፍ ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት አስበዉ ሚያዚያ 16 ቀን 2015 ዓ.ም በግምት 10:00 ሰዓት ሲሆን በሸገር ከተማ አስተዳደር መልካ ኖኖ ክ/ከተማ መልካ ገፈርሳ ወረዳ ልዩ ስሙ ወይብላ ማርያም ተብሎ በሚጠራዉ አካባቢ የንግድ ምልክትነቱ አርማ የዜኒት የፀጉር ቅባት ሆኖ ንብረትነቱ የዜኒት ገብስ እሸት ኢትዮጵያ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር የሆነ በንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ "ዜኒኒ" ተብሎ በቁጥር LTM/413/2006 ሚያዚያ 03 ቀን 2005 ዓ.ም የተመዘገበ ቀባቶችን፣ የፀጉር እና የሰዉነት ኮስሞቲክስ እንዲሁም የተለያዩ የንጽህናና የዉበት መጠበቂያ ምርቶችን በማምረት ለረጅም ዓመታት ሲጠቀምበት የቆየዉን የንግድ ምልክት መብቱን በግልጽ በመጣስ ዜኒት የሚል ጽሕፈት በላዩ ላይ የተቀረጸ እና የተለጠፈበት ጥርሙስ ዜኒት ገብስ እሸት ኢትዮጵያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የሚል አርማ በመጠቀም ተመሳስሎ የተሠራ ፈሳሽ የፀጉር ቅባት ስሙ ኦክሊቫ የሚባለዉን ወደዚህ የግል ማህበር ጠርሙስ በመጨመር በወይብላ ማሪያም አካባቢ በጋራ በማምረት 2ኛ የዜኒት ምርት በማለት ለገበያ አቅርበዉ ተገኝተዋል፡፡ ተከሳሾች የባለቤትነት መብት ሳይኖራቸዉ በሕገ-ወጥ መንገድ በሌላ ሰዉ የንግድ ምልክት በመጠቀም የማታለል እና የማምታታት ወንጀል በመፈጸም የዜኒት ገብስ እሸት ኢትዮጵያ ኃ/የተ/የግ/ማህበርን መልካም ስም እና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም በመጉዳት ለሀገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት በሚያስገኘዉ ከፍተኛ የግብር ገቢ ላይ ከፍተኛ ጉዳት በማድረሳቸዉ፤ በተለይም 2ኛ ተከሳሽ በተመሳሳይ የፀጉር ቅባት ምርት ላይ በራሱ ስም የንግድ ፍቃድ ባይኖረዉም በአመልካች ላይ በመደገፍ በሀሳቡና በድርጊቱ ሁሉ የወንጀል ድርጊቱን እና በሚያስገኘዉ ጥቅም ተካፋይ በመሆን በጋራ በፈጸሙት በሌላ ሰዉ የንግድ ምልክት የመጠቀም ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነዉ፡፡

ሁለቱም የስር ተከሳሾች የእምነት ክህደት ቃላቸዉን ሲጠየቁ በክሱ የተገለጸዉን የወንጀል ድርጊት አለመፈጸማቸዉን ገልጸዉ በመካዳቸዉ የስር ፍ/ቤት የዐ/ሕግ ማስረጃዎችን ሰምቶና መርምሮ እንዲከላከሉ ብይን ሰጥቷል፡፡ በመቀጠለም የተከሳሾችን የመከላከያ ምስክሮችን ከሰማ በኃላ ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙ ማስረጃዎች መርምሮ ተከሳሾችን በተከሰሱበት የሕግ ድንጋጌ ስር የተመለከተዉን በመተላለፋቸዉ ጥፋተኛ በማድረግ አመልካችን በ4(አራት) ዓመት ጽኑ እስራት እንዲሁም የስር 2ኛ ተከሳሽን ደግሞ በ5(ኣምስት) ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ ተከሳሾቹ በዚህ የጥፋተኝነትና ቅጣት ዉሳኔ ቅር ተሰኝተዉ በየደረጃዉ ላሉት ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎቶች ቅሬታ ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ በዚህ የጥፋተኝነትና ቅጣት ዉሳኔ እንዲሁም ቅጣት እንዲገደብ ያቀረቡት የገደብ ጥያቄ ተቀባይነት ባጣበት ዉሳኔ ባለመስማማት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

ተከሳሾቹ መጋቢት 26 ቀን 2016 ዓ.ም የተዘጋጀ 4 ገጽ የሰበር አቤቱታ በጋራ ያቀረቡ ሲሆን 2ኛ ተከሳሽ የነበረዉ ቴዎድሮስ ንጉሴ ያቀረበዉ የሰበር አቤቱታ ሙሉ በሙሉ እና አመልካች በጥፋተኝነትና ቅጣት ዉሳኔዉ ላይ ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ በዚህ መዝገብ ግንቦት 22 ቀን 2016 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ ለሰበር አያስቀርብም ተብሎ ዉድቅ የተደረገ በመሆኑ በዚህ ፍርድ አልተካተተም፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ያስቀርባል የተባለዉ በአመልካች ላይ የተወሰነዉ የጽኑ እስራት ቅጣት ሳይገደብ የታለፈበትን አግባብ ለማጣራት ሲሆን በዚህ ረገድ የቀረበዉ ቅሬታ ይዘት በአጭሩ፡- በስር ፍ/ቤት አመልካች ቅጣቱ በፈተና ጊዜ እንዲገደብላቸዉ መጠየቃቸዉን፤ ምክንያታቸዉም አመልካች የካንሰር ታማሚ ሆነዉ በመጨረሻ ደረጃ ላይ ስለሚገኙ፤ ለአቅመ አዳምና ሔዋን ያልደረሱ 3 ልጆችን የሚያሳድጉ መሆናቸዉን ነዉ፡፡ የስር ፍ/ቤት ወንጀሉ በሀገር ኢኮኖሚ ላይ የተፈጸመ በመሆኑ ቅጣቱ መገደብ የለበትም በማለት የገደብ ጥያቄያቸዉን ዉድቅ ማድረጉ ተገቢ አይደለም፡፡ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 171403 እና 177216 ቅጣትን ከመገደብ ጋር ተያይዞ ከሰጠዉ ገዥ ትርጉም ጋር የሚቃረን ዉሳኔ ነዉ፡፡ በወ/ሕጉ አንቀጽ 194 ቅጣትን ላለመገደብ የተቀመጡ ግልጽ ክልከላዎች ያሉ ሲሆን ወንጀሉ በሀገር ኢኮኖሚ ላይ የተፈጸመ አይደለም እንጂ ተፈጽሟል ቢባል እንኳ በክልከላ ምክንያትነት አልተቀመጠም፡፡ ተከሳሾች የ3 ሕጻናት አባትና እናት ሆነዉ ሁለቱም እስር ላይ በመገኘታቸዉ ከልጆች መብትና ጥቅም አንጻር ሲታይ የሁለቱም ወላጆቻቸዉ እስር ላይ መቆየት ልጆችን ሜዳ ላይ የሚበትንና መልካም ዜጋ ሆነዉ ለማደግ የወላጆቻቸዉ ቁሳዊና ስነ-ልቦናዊ ድጋፍ የሚፈልጉ ከመሆናቸዉ አንጻር መብታቸዉን እጅጉን የሚጎዳ ነዉ፡፡ ስለሆነም የአመልካች የገደብ ጥያቄ ዉድቅ መደረጉ በሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 171403 እና 177216 የሰጠዉን አስገዳጅ ትርጉም የሚቃረን በመሆኑ ስህተቱ ታርሞ በገደብ እንዲለቀቁ እንዲወሰን የሚጠይቅ ነዉ፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች ታማሚ መሆኗንና የሦስት ህጻናት እናት ከመሆኗ አኳያ ያቀረበችዉ የገደብ ጥያቄ መታለፉ ተገቢ መሆን አለመሆኑ ሰበር ችሎት በሰ/መቁ 171403 እና 177216 ላይ ከሰጠዉ ገዥ ዉሳኔ አንጻር ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ነዉ፡፡

ተጠሪ ሰኔ 07 ቀን 2016 ዓ.ም የተዘጋጀ 3 ገጽ መልስ ያቀረበ ሲሆን ይዘቱ በአጭሩ፡- አመልካች በወ/ሕ/አንቀጽ 192 እና 194 በገደብ ለመለቀቅ የሚያስችላቸዉን መስፈርቶችን አሟልተዉ አልተገኙም፡፡ ምክንያቱም አመልካች የተከሰሱበት ወንጀል የሌላ ሰዉ የንግድ ድርጅት ላይ ጉዳት አድርሰዋል የሚል ሲሆን ለተጎጂዉ አካል የሚገባዉን ካሳ ስላልከፈሉ እና የፈጸሙትን ወንጀል ስላላመኑ በሕግ የተቀመጠዉን መስፈርት ስላላሟሉ የቅጣታቸዉ አፈጻጸም እንዲታገድ አለመደረጉ ተገቢ በመሆኑ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች ሰኔ 25 ቀን 2016 ዓ.ም የተዘጋጀ 3 ገጽ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸዉን በሚያጠናክር መልኩ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን የአመልካችን አቤቱታ ከስር ፍ/ቤቶች ዉሳኔና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ አቤቱታዉ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ለሰበር ያስቀርባል የተባለዉ አመልካች ታማሚ መሆኗንና የሦስት ህጻናት እናት ከመሆኗ አኳያ ያቀረበችዉ የገደብ ጥያቄ መታለፉ ተገቢ መሆን አለመሆኑን ሰበር ችሎት በሰ/መቁ 171403

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

እና 177216 ላይ ከሰጠዉ ገዥ ዉሳኔ አንጻር ለመመርመር ነዉ። አመልካች በገደብ ለመፈታት ላቀረበችዉ ጥያቄ በምክንያትነት የጠቀሰችዉ አመልካች ታማሚ እና የ3 ሕጻናት ልጆች እናት መሆኗን ሲሆን የስር ፍ/ቤት የአመልካችን የገደብ ጥያቄ ዉድቅ ያደረገዉ ወንጀሉ የንግድ ምልክትን ያላግባብ በመጠቀም የተፈጸመ እና በሀገር ኢኮኖሚ ላይ የተፈጸመ በመሆኑ አመልካች ቅጣቱ እንዲገደብ ያቀረበችዉ ምክንያት የወ/ሕግ አንቀጽ 192 እስከ 197 ስር የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የማያሟላ ነዉ በሚል ነዉ።

በመሠረቱ ቅጣት ሊገደብ የሚችለው ጥፋተኛ የተባለን ሰው ለጥፋቱ መነሻ የሆኑትን ምክንያቶችን በጠቅላላው በመመልከት በተለይ ቅጣቱ ከመፈጸሙ በፊት ቅጣቱ ታግዶለት አመሉ ቢፈተን ሁለተኛ ጥፋት ከማድረግ የሚታገድ መሆኑንና ስለጠባዩም መሻሻል አንድ ጽኑ ማስጠንቀቂያ ብቻ የሚበቃ መሆኑ በፍ/ቤቱ ሲታመንበት በጥፋተኛው ላይ የተወሰነውን ቅጣት ለጊዜው በገደብ እንዲታገድ በማድረግ የወንጀለኛውን ጠባይ ለማረምና ለማሻሻል እንዲሁም ወደ መደበኛ ማህበራዊ ኑሮው ለመመለስ ሲባል የሚደረግ ስለመሆኑ ከወ/ሕግ አንቀጽ 192 እና የቅጣት ገደብን አስመልክቶ ከተደነገጉት ሌሎች የወንጀል ሕጉ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል። የቅጣት አፈጻጸምን መገደብ የማይቻለዉ ጥፋተኛዉ ከዚህ በፊት የጽኑ እስራት ቅጣት ወይም ከሦስት ዓመት የሚበልጥ የቀላል እስራት ቅጣት ተፈርዶበት እንደሆነና እንደገናም በተከሰሰበት ወንጀል ከእነዚህ ቅጣቶች አንዱ የሚወሰንበት እንደሆነ ወይም፤ ከዚህ ቀደም ያልተቀጣ ሆኖ አሁን በተከሰሰበት ወንጀል ከአምስት ዓመት የበለጠ የጽ እስራት ቅጣት የሚፈረድበት እንደሆነ ነዉ በማለት የወ/ሕግ አንቀጽ 194(1) ደንግጓል። ከዚህ መገንዘብ የሚቻለዉ በተለይ ከዚህ ቀደም ያልተቀጣ ጥፋተኛ በተከሰሰበት ወንጀል ከ5 ዓመት የበለጠ ጽኑ እስራት እስካልተቀጣ እና በወ/ሕ/አንቀጽ 197(1) ስር የተመለከቱትን ጥፋተኛዉ በመልካም ጠባይ እንደሚመራ፣ እንዲፈጽም የተሰጠዉን ግዴታ እንደሚቀበል ፍርድ ቤቱ እስካመነበት ድረስ ፍ/ቤት የወሰነዉን ቅጣት አፈጻጸም መገደብ የሚችል መሆኑን ነዉ።

ከላይ ከተገለጸዉ በተጨማሪ ጥፋተኛዉ ቅጣቱ እንዲገደብለት ያቀረባቸው ምክንያቶች የጥፋተኛዉን የቀድሞ ታሪክ፤ የጠባዩን እና የዓመሉን አካሄድ ለመመዘን የሚያስችሉ አሳማኝ እና በጥፋተኛዉ ላይ የተጣለው ቅጣት ታግዶ ቢቆይ ዳግም ጥፋት ከመፈጸም እንዲቆጠብ ለማድረግ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ሆነው ሳለ ፍ/ቤት ቅጣቱን መገደብ ሲገባው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194 ቅጣት እንዳይገደብ ለማድረግ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ውስጥ ያልተቀመጠውን መስፈርት መሠረት በማድረግ የአመልካች የቅጣት ገደብ ጥያቄ ከአደጋው አሳሳቢነት አንጻር ተቀባይነት የለውም በማለት የገደብ ጥያቄዉን ዉድቅ ማድረጉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት መሆኑን የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 171403 ገዥ ትርጉም ሰጥተበታል።

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች ከዚህ ቀደም በሌላ ወንጀል የተቀጡበት ወንጀል ስለመኖሩ በተጠሪ በኩል ያልቀረበ በመሆኑና በዚህ መዝገብ በተያዘዉ ጉዳይ እንዲቀጡ የተወሰነባቸዉ 4 ዓመት በመሆኑ በወ/ሕግ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አንቀጽ 194(1/ለ) መሰረት ቅጣቱን ለመገደብ የሚከለክል የሕግ ክልከላ የለም፡፡ የስር ፍ/ቤት የተፈጸመዉ ወንጀል የሌላን ሰዉ የንግድ ምልክት ያለአግባብ መጠቀም በመሆኑ በሀገራዊ ኢኮኖሚ ላይ የተፈጸመ ስለሆነ የአመልካች የገደብ ጥያቄ በወ/ሕግ አንቀጽ 192 እስከ 197 የተዘረዘረዉን መስፈርት አያሟላም በሚል ነዉ፡፡ ሆኖም የወ/ሕግ አንቀጽ 194(1) የተወሰነዉን የቅጣት ክብደት መነሻ በማድረግ ለመጀመሪያ አጥፊ ከ5 ዓመት የበለጠ ጽኑ እስራት ለተቀጣ አጥፊ ቅጣቱ እንዳይገደብለት ክልከላ አደረገ እንጂ የሌላን ሰዉ የንግድ ምልክት ያለአግባብ መጠቀም በአገር ኢኮኖሚ ላይ የተፈጸመ ወንጀል መሆኑን የለየና ቅጣቱም ሊገደብ እንደማይገባ ክልከላ ያደረገ አይደለም፡፡ በዚህ አግባብም ለተጠቀሰዉ ወንጀል የተወሰነ ቅጣት እንዳይገደብ በልዩ ሁኔታ ክልከላ ያደረገ የወንጀል ሕግ ድንጋጌ የለም፡፡ ስለሆነም የስር ፍ/ቤት የአመልካችን የገደብ ጥያቄ ዉድቅ ለማድረግ የሰጠዉ ምክንያት የወ/ሕግ አንቀጽ 194 እና 197 የተመለከቱትን መስፈርቶች ያላሟላና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 171403 የሰጠዉን ገዥ ትርጉም ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ ነዉ፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ቅጣቱ እንዲገደብላቸዉ ያቀረቡት ምክንያት ከስር 2ኛ ተከሳሽ ጋር በነበራቸዉ ጋብቻ ዉስጥ ያፈሯቸዉ የሚስተዳድሯቸዉ 3 ልጆች ያሏቸዉ መሆኑ ሕጻናቶቹ ከአባታቸዉ በተጨማሪ እናታቸዉ በመታሰራቸዉ ምክንያት ሕጻናት ልጆች ለዕድገታቸዉ የሚሆን ቁሳዊም ሆነ ስነ-ልቦናዊ ድጋፍ የሚያጡ ከመሆናቸዉም በተጨማሪ አመልካች መጨረሻ ደረጃ የደረሰ የጡት ካንሰር ታማሚ በመሆናቸዉ ቅጣቱ ሊገደብ ይገባል የሚል ነዉ፡፡ እነዚህ ሁለት ምክንያቶች በስር ፍ/ቤት በማስረጃ ተረጋግጠዉ በቅጣት ማቅለያነት ለአመልካች የተያዙ ናቸዉ፡፡ በተለይ አመልካች የተወሰነባቸዉን የእስራት ቅጣት በማረሚያ ቤት ሆነዉ እንዲፈጽሙ ቢደረግ ሕጻናት ልጆቻቸዉ የሁለቱን ወላጆቻቸዉን ድጋፍ የሚያሳጣቸዉ በመሆኑ በሕጻናቱ ላይ ቁሳዊም ሆነ ህሊናዊ ጫና የሚደርስባቸዉ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ እንዲህ በሆነ ጊዜ ደግሞ ፍ/ቤቶች የሕጻናትን ደህንነት በቅድሚያ የማረጋገጥ ሕገ-መንግስታዊ ግዴታ ያለባቸዉ በመሆኑ በወንጀል ሕጉ ቅጣት ለመገደብ የተቀመጡ ሁኔታዎች መሟላታቸዉን በማረጋገጥ ቅጣት እንዳይፈጸም ማገድ እንደሚገባ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 177216 በሰጠዉ ገዥ ትርጉም መሠረት አመልካች የተወሰነዉ የእስራት ቅጣት በስር ፍ/ቤቶች አለመገደቡ ስህተት ነዉ፡፡

ሲጠቃለል አመልካች የተወሰነባት የአራት ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት እንዲገደብላት ያቀረበቻቸዉ ምክንያቶች በአመልካች ላይ የተጣለው ቅጣት ታግዶ ቢቆይ ዳግም ጥፋት ከመፈጸም እንዲትቆጠብ ለማድረግ የሚያስችሉ ሁኔታዎች የሚያሟሉ ከመሆናቸዉም በላይ አመልካች የእስር ቅጣቱን በሙሉ እንዲትፈጽም ቢደረግ በሕጻናት ልጆቿ ላይ የሚደርሰዉን ቁሳዊና ስነ-ልቦናዊ ጫና ከግምት በማስገባት ቅጣቱን መገደብ ሲገባው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194 ቅጣት እንዳይገደብ ለማድረግ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ውስጥ ያልተቀመጠውን መስፈርት መሠረት በማድረግ የአመልካች የቅጣት ገደብ ጥያቄ ወንጀሉ በንግድ ምልክት ላይ የተፈጸመ ነዉ በሚል ተቀባይነት የለውም በማለት የአመልካችን የገደብ ጥያቄ ውድቅ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በማድረግ የሰጠው ውሳኔ በወንጀል ሕጉ ቅጣት ስለሚገደብባቸው የተቀመጡትን ቅድመሁኔታዎች እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰ/መ/ቁ 171403 እና 177216 የሰጠዉን ገዥ ትርጉም ያላገናዘበ እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሸ) እና አንቀጽ 10(1) መሠረት መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በሸገር ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 76549 ጥር 07 ቀን 2016 ዓ.ም ተሰጥቶ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 356664 የካቲት 28 ቀን 2016 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ እና በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 452708 መጋቢት 16 ቀን 2016 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት በተሰጠ ትዕዛዝ የጸናዉ ዉሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1/ለ) እና በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 195(2) መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. በሸገር ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት በአመልካች ላይ ከተወሰነዉ የአራት ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት ዉስጥ ያልፈጸመችዉ ቀሪ የጽኑ እስራት ጊዜ በአራት ዓመት የፈተና ጊዜ ሳይፈጸም ተገድቦ እንዲቆይ ተወስኗል፡፡
3. በወ/ሕግ አንቀጽ 197 መሰረት አመልካች ለገባችዉ የገደብ ግዴታ አፈጻጸም መተማመኛ ዋስትና ይሁን ዘንድ ብር 20,000(ሃያ ሺህ ብር) የሚበቃ ዋስ ታቅርብ ወይም ገንዘቡን እንድታሲዝ ታዟል፡፡ አመልካች የገደብ አፈጻጸም ዋስትና ግዴታ ስትገባ ግንቦት 22 ቀን 2016 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ ያስያዘችዉ ገንዘብ እንዲለቀቅ ታዟል፡፡
4. የስር ፍ/ቤት አመልካችን ሆነ የስር 2ኛ ተከሳሽን አስመልክቶ የሰጠዉ ጥፋተኝነትና የቅጣት መጠን የዉሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡
5. መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

# በህዳር ወር 2017 የተወሰኑ

# 38 የሰበር ችሎት ውሳኔዎች

የሰበር መ/ቁ 193894

ህዳር 27 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች፡ ብርሃኑ አመነው

በእውቀቱ በላይ

ገበየሁ ፈለቀ

መላኩ ካሳዬ

ማርታ ተካ

አመልካች፡- ወ/ሮ ድላይ አማረ

ተጠሪዎች፡- 1) ወ/ሮ ለታይ ደሳለኝ

2) ወ/ሮ ለተኪዳን ሃጎስ

3) ወ/ሮ ዘነቡ ታደለ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

መዝገቡ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበዉ የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ የህግ ስህተት የለዉም በማለት በመ/ቁ/121980 ላይ በቀን

22/05/2012ዓ.ም የሰጠዉ ትእዛዝ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል፤በሰበር ችሎት እንዲታረም በማለት አመልካች ጠበቃ በቀን 04/12/2012ዓ.ም ጽፎ ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ ነዉ፡፡

ጉዳዩ አመጣጥ ከመዝገቡ እንደተገነዝበነዉ ክርክሩ የእርሻ መሬት ይዞታ የሚመለከት ሲሆን በስር ፍርድ ቤት ከሳሽ አመልካች ሲሆኑ ተጠሪዎች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በሳምረ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 04501 በቀን 19/03/2012 ባቀረበችው ክስ የሳምረ ከተማ ነዋሪ ሲሆን በ1979 ዓ.ም የተሰጠኝን በዓምዲ ወያነ ደብረሓይላ የሚገኝ የእርሻ መሬት ይዞታዬን ተጠሪዎች ከ2009 ዓ.ም ጀምሮ የያዙት ሲሆን 1ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ደብረገነት ተብሎ በሚታወቅ ቦታ የካርታ ቁጥር 10701010-01881 የሆነ እንዲሁም ቀብቀብ በተባለ ቦታ የካርታ ቁጥር 13784 የሆነ ይዞታ፤ 2ኛ ተጠሪ በበኩሏ ሓዱሽ ቀኒ በተባለ ቦታ የካርታ ቁጥር 00827 አዋሳኞቸው በክሱ የተጠቀሰውን ይዞታዬን ይዘውብኛል፤ የእድሜ ባለፀጋ በመሆኔ በመሬት የመጠቀም መብቴን ልነጠቅ አይገባም ፤በ27/13/2005ዓ.ም የቀበሌው መሬት አስተዳደር መሬቴን እንዳልቀማ ወስኗል፡፡በመሆኑም ይዞታዬን ለቀው እንዲያስረክቡኝ በማለት ዳኝነት የጠየቀች መሆኑን፤ተጠሪዎች በ27/07/2011ዓ.ም በሰጡት መልስ የመሬት እደላ የተካሄደው በ1974 ዓ.ም በህንፃሎ ወረዳ ደብረኃይላ ቀበሌ መገንዓ በተባለ መንደር እንጂ በ1979 አይደለም፤አመልካች በወቅቱ በቦታው አልነበሩም፤መሬቱ የተሰጣቸው ከደርግ ሰፈራ በ1984 ዓ.ም ሲመለሱ ነው፤ መሬቱ የተሰጣቸው በዓምዲ ወያነ ደብረኃይላ ቀበሌ መገንዓ መንደር ነዋሪ ሆነው ነው፤ወደ ሳምረ ከተማ የሄዱትም በ2000 ዓ.ም ሲሆን የሄዱት ጧሪ አጥተው እንዲጦሩ ሳይሆን ጠላ ሸጠው ለመተዳደር ነው ፤ቀበሌው መሬታቸውን በ2008 እንዲነጠቁ በማድረግ ለተጠሪዎች በሽግሽግ ዕጣ ወጥቶ ተሰጥቶናል፤አመልካች ጤነኛና ሰርተው መኖር የሚችሉ ናቸው ክሱ ውድቅ ይደረግልን በማለት መከራከራቸዉን መዝገቡ ያሣያል፡፡

የስር ፍርድ ቤትም አመልካች መሬቱን ያገኙት በሳምረ ከተማ እያሉ ለመሆኑ፤ መተዳደሪያቸው በእርሻ ስለመሆኑ፤ወደ ሳምረ ከተማ የሄዱት በሽምግልና ጧሪ አጥተው እንዲረዱ መሆን አለመሆኑን እንዲሁም መሬታቸው ተላልፎ የተሰጠበትን ሁኔታ አግባብነት ጭብጥ ይዞ ካጣራ በኃላ ከግራቀኙ ምስክር የመሬት አስተዳደር ባለሙያዎቹ መሬቱን ለሌላ ያደሉት ለአመልካች እንደታደለ ሳያውቁ ነው፤አጣርተው መስጠት ነበረባቸው የሚባል ቢሆንም እንኳን ስነ-ስርዓትን ተከትሎ ማስታወቂያ ተለጥፎ እና በምክር ቤት ፀድቆ ስለሆነ ለሌላ ያደሉበት መንገድ በአግባቡ ነው፤ በአዋጅ ቁጥር 239/06 አንቀፅ 11(5)(ነ) በደማቸው

ኤች አይ ቪ ካላቸው ውጭ ሌላ ህመም ያላቸው ሰዎች መሬታቸው ተላልፎ እንዳይሰጥ ምክንያት ሊሆን እንደማይችል ተቀምጧል ፤በ2007 ዓ.ም ከሃላፊነታቸው የተነሱት የቀበሌው መሬት አስተዳደር ባለሙያዎች የአመልካች መሬት የተመለሰላቸው ለመሆኑ የሚያሳይ ውሳኔ በ2008ዓ.ም ለመጡት አዲስ አስተዳደሮች አላሳወቋቸውም፤አመልካች መሬታቸውን ያጡበት ምክንያት ሌላ ከተማ ስለሚኖሩና ጧሪ አጥተው ስላልሄዱ በመሆኑ ለተጠሪዎች የተሰጠበት መንገድ  በአግባቡ ነው ለአመልካች አይገባቸውም ሲል አመልካች ወጪና ኪሳራ 800 ብር እንዲከፍሉ ወስኗል ፡፡

አመልካች በውሳኔዉ ቅር ተሰኝተዉ ይግባኝ ለደቡባዊ ምስራቅ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/መ/ቁ/13212 በቀን 17/04/2012 አቅርበው ፍርድ ቤቱ አያስቀርብም ሲል መዝገቡን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 337 መሰረት የሰረዘ ሲሆን ቀጥሎም አቤቱታቸውን ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ችሎት በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት አልተፈፀመም ሲል መዝገቡን ዘግቷል፡፡ለሰበር ችሎቱ አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ በቀን 04/12/2012 ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይዘትም፡-አመልካች አቅመ ደካማ እና የጤና ችግር ያለብኝን መሆኑን በቀበሌው ስለተረጋገጠ ተወስዶብኝ የነበረው የእርሻ መሬት የተመለሰልኝ ለመሆኑ የቀረበውን የሰነድ እና የሰው ምስክርነት ወደ ጎን በመተው ለተጠሪዎች መሰጠቱ ትክክል ነው ሲል የስር ፍርድ ቤት መወሰኑ የትግራይ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደር አዋጅ አጠቃላይ ይዘትና ድንጋጌ በሚገባ ካለመረዳት የተሰጠ ዉሳኔ ነው፤አመልካች እድሜ ከ65 ዓመት በላይ እንደሆነ በሚገባ ያስረዳሁ ቢሆንም ተቃራኒ ማስረጃ ባልቀረበበት በአካል ሲታዩ አዛውንት አይመስሉም በሚል የተደረሰበት ድምዳሜ ግለሰባዊ ምልከታ የተንፀባረቀበት እንጂ እንደ ማስረጃ ሊወሰድ አይገባም፤አመልካች ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ ለአዛውንቶች በማህበራዊ ጉዳይ በሚደረግ እርዳታ ተካትቼ ድጋፍ የሚደረግልኝ ለመሆኑ ተጨማሪ የሰነድ ማስረጃ አያይዤ ያቀረብኩ ሲሆን የሥር ፍ/ቤት ይህን ግንዘቤ ውስጥ ሳይከት ውሳኔ ሰጥቷል፤የትግራይ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 136/2000 አንቀፅ 12(2)(በ) እና ይህን ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁ239/2006 አንቀፅ 11(5) ጧሪና ተንከባካቢ የሌላቸው አዛውንቶች እና አቅመ-ደካሞች መሬታቸው ከሚገኘው ቀበሌ ቢለቁም መሬታቸውን እንደማይነጠቁ ቢደነግጉም የስር ወረዳ ፍርድ ቤት ይህን በመጣስ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ወስኗል፡፡በመሆኑም ውሳኔው ተሽሮ ያለአግባብ የተወሰደብኝ የእርሻ መሬት እንዲመለስልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

አቤቱታውን የመረመረው የሰበር አጣሪ ችሎት ለክርክሩ ምክንያት የሆነው የገጠር መሬት ከአመልካች ተነጥቆ (ተወስዶ) ለተጠሪዎች የተሰጠበት (የተላለፈበትን) አግባብ ከክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር አዋጅ ጋር በማገናዘብ ለማጣራት ተጠሪዎች መልሳቸውን እንዲያቀርቡ ነሃሴ 26 ቀን 2012 ዓ.ም ትዕዛዝ የሰጠ ሲሆን ተጠሪዎች መጥሪያ ደርሷቸው መልስ ባለማቅረባቸው የሰበር ችሎቱ ነሃሴ 16 ቀን 2016 ዓ.ም በሰጠዉ ትእዛዝ መልስ የመስጠት መብታቸውን አልፎታል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ያስቀርባል ሲባል የተያዘውን ጭብጥ ከግራቀኙ ክርክር፤ በስር ፍርድ ቤት በማስረጃ ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር እና ከተገቢው የህግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ከመዝገቡ እንደተገነዘብነዉ ለክርክር ምክንያት የሆነዉ ይዞታ ከአመልካች የተነጠቀዉ አመልካች ቀበሌዉን ለቀዉ ወደ ከተማ ገብተዋል በሚል ምክንየት ተነስቶ ለተጠሪዎች የተደለደለ ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ፍሬነገር ጉዳይ ነዉ፡፡አመልካች አጥብቀዉ የሚከራከሩት አቅመደካማ እና ጧሪ በማጣት ወደ ከተማ መግባታቸዉን ጠቅሰዉ በዚህ ምክንያት የገጠር መሬት ይዞታቸዉ ሊነጠቅ እንደማይገባ የክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ የሚደነግግ ስለመሆኑ በመግለጽ የስር ፍርድ ቤቶች የህግ ስህተት ፈጽመዋል በማለት ነዉ፡፡እኛም ይህንኑ መሰረት በማድረግ አግባብነት ካለዉ የህግ ድንጋጌ አንጻር ተመልክተናል፡፡

የትግራይ ክልል የገጠር መሬት አዋጅ የገጠር መሬት ይዞታ መብት የሚታጠበትን ምክንያት በዝርዝር ደንግጓል፡፡አዋጅ ቁጥር 136/2000 በአዋጅ ቁጥር 239/2006 እንደተሻሻለዉ የገጠር መሬት ይዞታ መብት የሚታጠበትን ዝርዝር ሁኔታ በአዋጁ በአንቀጽ 11 ስር የተመለከተ ሲሆን ከዚህ ዉስጥ አንዱ ምክንያት ባለይዞታዉ መሬቱ የሚገኝበትን ቀበሌ ለቆ ሲሔድ ይዞታዉ ተነስቶ ለሌላ ሰዉ የሚተላለፍ ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ነገር ግን ህጉ በልዩ ሁኔታ የለያቸዉ የመሬት ባለይዞታ የሆኑ ሰዎች ከቀበሌዉ ቢለቁም መሬታቸዉን ሊነጠቁ እንደማይገባ ተመልክቷል፡፡ከዚህ ልዩ ሁኔታ ዉስጥ አንደኛዉ ባለይዞታዉ አቅመዳካማ እና ጧሪ በማጣት ከቀበሌዉ ሲለቅና እና ይህም በሚመለከተዉ የቀበሌ አስተዳደር ሲታመንበት

ባለይዞታዉ ከቀበሌ ቢለቅ እንኳን መሬቱ እንደማይነጠቅና ለሌላ ሰዉ እንደማይሰጥ በአንቀጽ 11(5/በ) ስር ተደንግጎ እናገኛለን፡፡ የአመልካች መከራከሪያ ምክንያትም ይህንኑ መሰረት ያደረገዉ ነዉ፡፡የስር ፍርድ ቤትም ይህንኑ ድንጋጌ ጠቅሶ እያለ የአመልካችን ክርክር ዉድቅ ያደረገዉ በአንድ በኩል አመልች በቀበሌዉ የሚትኖር ልጅ አላት በማለት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች በአካል ሲታዩ አቅም አጥተዉ ተንከባካቢ የሚፈልጉ አይመስልም የሚል የራሱን እይታ ወይም ግንዛቤ በመጨመር ስለመሆኑ ዉሳኔዉ ይዘት ያሣያል፡፡

በመሰረቱ አንድ አከራካሪ ፍሬነገር ጉዳይ ላይ ፍርድ ቤት ዳኝነታዊ ግንዛቤ (judicial notice) መዉሰድ የሚችለዉ ህጉ በግልጽ ሲፈቅደለት እና በገሀዱ ዓለም እዉነት ነዉ ተብሎ የሚገመቱ ሁኔታዎች ላይ ብቻ ስለመሆኑ የማስረጃ አቀባበል መሰረታዊ መርህ የሚያስገነዝበን ጉዳይ ነዉ፡፡በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች በእድሜ የገፉ አዛዉንት መሆናቸዉን ጠቅሰዉ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት ያለዉ መሆን አለመሆኑን አካላዊ ምልከታ መሰረት አድርጎ ፍርድ ቤቱ የራሱን ድምዳሜ እንዲወስድ የሚያስችል የህግ መሰረት የለዉም፡፡ይልቁንም በዚህ ረገድ የቀበሌዉ አስተዳደር አምኖበት የአመልካች መሬት ሊነጠቅ አይገባም ተብሎ በአስተዳደር አካል በ2005ዓ.ም እንዲመለስላቸዉ የተወሰነ መሆኑ ተረጋግጦ ባለበት ሁኔታ በ2008ዓ.ም የአመራር ለዉጥ በመደረጉ አዲሶቹ አመራሮች ይህንን ሳያጣሩ የአመልካችን መሬት ነጥቀዉ ለተጠሪዎች መስጠታቸዉ ስህተት መሆኑን የሥር ፍርድ ቤት በፍርዱ ላይ በግልጽ አስፍሮ እያለ ራሱ ካረጋገጠዉ ፍሬነገር በተቃራኒ መሬቱ ለአመልካች ሊመለስ አይገባም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ የተረጋገጠዉን ፍሬነገር ያገናዘበ አይደለም፡፡በክርክሩ ሂደት የተረጋገጠዉን ፍሬነገር ወደጎን በመተዉ የሚሰጥ ፍርድ መሰረታዊ የሆነ ህግ ስህተት ስለመሆኑ እና በሰበር ችሎቱ ሊታረም የሚገባ ስለመሆኑ ይህ ሰበር ችሎት በተለያዩ መዝገቦች የሰጠዉ ገዥ ዉሳኔ ያስገነዝባል፡፡(ሰበርመ/ቁ/44804፣229926፣ 229475 እና ሌሎች መዝገቦችን ይመለከቷል፡፡)

በመሰረቱ አንድ ጉዳይ በሰበር ችሎት ሊታይ የሚችለው የመጨረሻ ዉሳኔ ያገኘ ሆኖ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4) እና አንቀጽ 10 ስር ከተመለከቱት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መመዘኛ አንዱን ወይም ከአንድ በላይ ድንጋጌ አሟልቶ ሲገኝ ነው፡፡በተለይም በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ /ትዕዛዝ/ ብይን ሲሆን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታዉን ተቀብሎ በሰበር የማየት ስልጣን የሚኖረዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ

ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ የሚቃረን ሲሆን እንዲሁም አግባብነት የሌለዉን ህግ በመጥቀስ ወይም ህግን ያላግባብ በመተርጎም የተሰጠ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሆኖ ጉዳዩም አገራዊ ፋይዳን የሚመለከት ሲሆን ብቻ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 10 (1/ሐ/ እና /መ) ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ከዚህም የምንረዳዉ የሰበር አቤቱታ የቀረበበት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ ከእነዚህ ሦስቱ ሁኔታዎች ዉጪ ባሉት ሁኔታዎች፣ መሠረታዊ የህግ ስህተትን መስፈርት አስመልክቶ በአዋጁ አንቀጽ 2(4)ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ዉስጥ አንዱን የሚያሟላ ሆኖ ቢገኝ እንኳን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በሰበር የማረም ስልጣን የሌለዉ መሆኑን ነዉ፡፡ስለሆነም ይህ የፌዴራል ጠቅላይ ሰበር ሰሚ ችሎት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን በመቃወም የቀረበለት አቤቱታ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ስራ ላይ ከዋለ በኋላ ከሆነ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን ያለመሆኑን በመወሰን ረገድ እነዚህኑ ልዩ ሁኔታዎች ማለትም በአዋጁ አንቀጽ 10(1/ሐ/መ) ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ከግምት ዉስጥ የማስገባት ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

በዚህ ጉዳይ ክርክር የተነሳበት ይዞታ አስቀድሞ ለአመልካች ተደልድሎ ሲጠቀሙበት ቆይተዉ ቀበሌዉን ለቀዉ ወደ ከተማ መግባታቸዉ፤አመልካች ቀበሌዉን የለቀቁት አቅመደካማ እና ጧሪ ፍለጋ ስለመሆኑ በቀሌዉ አስተዳደር ተረጋግጦ በ2005ዓ.ም መሬቱ እንደመለስላቸዉ ከተወሰነ በኋላ በ2008ዓ.ም ያለአግባብ ተወስዶ ለተጠሪዎች መደልደሉ አቅመደካማ እና ጧሪ ያጣ ሰዉ ቀበሌዉን በመልቀቁ መሬቱ አይነጠቅም የሚለዉን የክልሉን የገጠር መሬት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 239/2006 አንቀጽ 11(5/በ) ግልጽ ድንጋጌ በሚቃረን አኳኋን የተወሰደ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ከተረጋገጠ ፍሬነገር ተገንዝበናል፡፡ስለሆነም የወረዳዉ ፍርድ ቤት ይህንኑ አረጋግጦ እያለ መሬቱ ለአመልካች አይመለስም ሲል የደረሰበት ድምዳሜ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጠዉን ፍሬነገር እና አመልካች እና ተመሳሳይ ምክንያት ያላቸዉን ሰዎች መብት ለመጠበቅ የተዘረጋዉን ህግ ይዘት እና ዓላማ ያላገናዘበ ነዉ፡፡የክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶችም ይህንኑ ሳያርሙ ማለፋቸዉ ስህተት ነዉ፡፡

ሲጠቃለል አመልካች ቀበሌዉን ለቀዉ የሄዱበት ምክንያት አቅመደካመ እና ጧሪ ፍለጋ ስለመሆኑ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጠዉ ፍሬነገር በመሆኑ እንዲህ በሆነ ጊዜ ደግሞ የገጠር መሬት ባለይዞታ መብት የማያሣጣ ስለመሆኑ በልዩ ሁኔታ በክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ የተደነገገ ከመሆኑ አንጻር ፍርድ ቤቱ የደረሰበት ድምዳሜ ሲታይ በህግ አተገባበርም ሆነ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

የተረጋገጠ ፍሬነገር ከህግ ጋር በማገናዘብ ዉሳኔ መሰጠትን በተመለከተ ሰበር ችሎቱ በተለያዩ መዝገቦች የሰጠዉን ገዥ ዉሳኔ የሚቃረን በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ ሸ) እና 10(1/ሐ) መሠረታዊ የሕግ ስህተት መፈፀማቸውን የሚያሳይ በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ውሳኔ**

1. በዚህ ጉዳይ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ዉሳኔም ሆነ ይህንኑ በማጽናት የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/121980 ላይ በቀን 22/05/2012ዓ.ም የሰጠዉ ትእዛዝ በፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ስነ- ስርኣት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 መሰረት ተሽሯል ፡፡
2. ክስ የቀረበበት መሬት ለአመልካች ሊመለስ ይገባል ብለናል፡፡የሳምረ ወረዳ ፍርድ ቤት በዚህ መሰረት እንዲያስፈጽም እንዲያስፈጽም የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ይተላለፍለት ብለናል ይጻፍ፡፡
3. አመልካች ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ዝርዝር ለሳምረ ወረዳ ፍርድ ቤት በማቅረብ መጠየቅ ይችላሉ ብለናል፡፡
4. የውሳኔው ትክክል ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ ፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

*የሰ/መ/ቁ 244423*
*ህዳር 24 ቀን 2017ዓ/ም*

**ዳኞች፡-** ብርሃኑ አመነዉ

ገበየሁ ፌለቀ

በዕዉቀት በላይ

መላኩ ካሳዬ

ማርታ ተካ

**አመልካች፡-** አቶ ተሾመ ጅንጋ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ አስቴር ቡጃ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ፍርድ</u>**

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው የገጠር መሬት ይዞታን የተመለከተ ጉዳይ ሲሆን የተጀመረው በአርቤጎና መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍ/ቤት ተጠሪ ከሳሽ ሲሆኑ አመልካች 2ኛ ተከሳሽ እንዲሁም አቶ ደበበ ለገሰ 1ኛ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ በሲዳማ ክልል የባንሳ አካባቢ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 05613 መስከረም 10 ቀን 2014 ዓ.ም የወረዳዉን ፍ/ቤት በመሻር የሰጠዉና በየደረጃዉ ባሉ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ችሎቶች በተሰጡ ዉሳኔዎች የጸናዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በሚል ነዉ፡፡

ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ: - የስር 1ኛ ተከሳሽና ተጠሪ ባልና ሚስት ሲሆኑ ክርክር ያስነሳዉንና አዋሳኞቹ በክሱ የተገለጸዉን በላዩ ላይ የቀርቀሀ ክዳን ቤት፤ እንሰት፤ ቀርከሀ፣ የዉጭ ጥድ፣ ባህር ዛፍ ያለበትን ይዞታ ተጠሪን ሳያሳዉቅና ደብቆ መጋቢት 09 ቀን 2006 ዓ.ም በተጻፈ ዉልበኮንትራት ለአመልካች ሰጥቷል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ የጋራ ይዞታዋን ፍቃዷን ባልሰጠችበትና በተንኮል የኮንትራት ዉል

የተደረገበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 658 እና 1808 መሰረት ዉሉ ፈርሶ የመሬት ይዞታዉ እንዲመለስላቸዉ እንዲወሰን ጠይቀዋል፡፡

የስር 1ኛ ተከሳሽ ለክሱ በሰጠዉ መልስ ገንዘብ ተቸግሮ መሬቱን ተጠሪ ባላወቁበት በብር 45,000 ማኮናተሩን ገልጾ፤ አሁን ተጠሪ ያወቀች በመሆኗ ዉሉ ፈርሶ መሬቱ ቢመለስ የማይቃወም መሆኑን በማገለጽ ተጠሪን በመደገፍ መልስ ሰጥቷል፡፡

የአሁኑ አመልካች በበኩሉ በሰጠዉ መልስ በክሱ አዋሳኙ የተገለጸዉ መሬት አመልካችና በባለቤቱ ስም የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ተሰጥቷቸዉ፤ በማሳ መለያ ቁጥር 00498 0.66 ሄክታር በሚል የሚታወቅና ግብር በስማቸዉ እየከፈሉ ከ14 ዓመት በፊት ጀምሮ መኖሪያ ቤት ሰርተዉበትና በርካታ ንብረት አፍርተዉበት የያዙት ይዞታቸዉ እንጂ ተጠሪ እንደሚሉት በዉል የያዙት አይደለም፡፡ ተጠሪ ያቀረቡት ዉልም ሆነ ምዝገባ ባለመኖሩ ክሱ ዉድቅ እንዲደረግ በመጠየቅ ተከራክሯል፡፡

በአርቤጎና መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶና አጣርቶ በተጠሪና በስር 1ኛ ተከሳሽ ዉል ስለመደረጉ የሚያስረዳ የዉል ሰነድም ሆነ ቅጅዉ አለመቅረቡን፤ ምስክሮችም ዉል ተደርጓል ሲባል ብቻ መስማታቸዉን እንጂ ሲፈራረሙ ያላዩ መሆናቸዉን፤ ይልቁንም ክርክር ያስነሳዉን የመሬት ይዞታ አመልካች የይዞታ ማረጋገጫ ያገኙበትና ለረጅም ጊዜ ይዞ ንብረት አፍርቶ የሚገኝበት የራሱ ይዞታ መሆኑ በሰዉና በሰነድ ማስረጃ ከመረጋገጡም በላይ በማጣራት ሂደት የተረጋገጠ ስለሆነ ይዞታዉ የአመልካች በመሆኑ ሊለቅ አይገባም በማለት የተጠሪን ክስ ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝተዉ ተጠሪ ባቀረቡት ይግባኝ መነሻነት ጉዳዩን የተመለከተዉ የባንሳ አካባቢ ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ መርምሮ ምንም እንኳ ተጠሪ የዉል ሰነድ ባያቀርቡም ተጠሪ እንዲፈርስ የጠየቁት ዉል ራሳቸዉ ያደረጉትን ዉል ሳይሆን ባለቤታቸዉ ከአመልካች ጋር ያደረጉትን ዉል በመሆኑ፤ ግብር የተገበረበትን ደረሰኝ ያቀረቡ በመሆኑና ምስክሮችም ዉል ስለመደረጉ የመሠከሩ ሲሆን የአመልካች ምስክሮች የተለያዩ ምስክርነት የሰጡ በመሆናቸዉ፤ አመልካች በሚስቱ ስም ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ ግብር የተከፈለበትን ደረሰኝ ቢያቀርቡም ከ14 ዓመት በፊት የያዝኩት ይዞታዬ ነዉ በማለት ካስመሰከሩት ጋር የሚጋጭ መሆኑን፤ የይዞታ ማረጋገጫዉ መቼ እንደተሰጣቸዉ የማይለይ በመሆኑ ተጠሪ ሳታዉቅ የተደረገዉ ሽያጭ ሕገ-ወጥ ነዉ በማለት የወረዳዉን ፍ/ቤት ዉሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝተዉ ባቀረቡት ይግባኝ መነሻነት ጉዳዩን የተመለከተዉ የሲዳማ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ መርምሮ በዉጤት ደረጃ የዞኑን ከፍተኛ ፍ/ቤት ዉሳኔ ሲያጸና ዉሉ እንዲፈርስ በማለት ወስኗል፡፡ በመቀጠል አመልካች ለክልሉ ሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም ግራ ቀኙን አከራክሮ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠዉን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘት፡- ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶች ተጠሪ እንዲፈርስ የጠየቁት የዉል ሰነድ ባልቀረበበት ከረጅም ጊዜ በፊት አመልካች ንብረት አፍርቶበትና ቤተሰብ መስርቶበት ከሚገኝበት ይዞታ የሚያፈናቅል ዉሳኔ መስጠታቸዉ ተገቢ አይደለም፡፡ ጉዳዩ የማይንቀሳቀስ ንብረት የሚመለከት እስከሆነ ድረስ ዉል አለ ለማለት የሚቻለዉ በሚመለከተዉ አካል የተመዘገበ ዉል ሲኖር ነዉ፡፡ ሆኖም በዚህ መልክ የተመዘገበ ዉል በሌለበት፤ ዉል ይፍረስ የሚል ክስ ተጠሪ መቅረባ ተገቢ አይደለም፡፡ ክርክር ያስነሳዉ ይዞታ አመልካች ለረጅም ዘመን ይዞ የተለያዩ ቋ ንብረቶች አፍርቶበትና ቤት ሰርቶበት የገጠር መሬት ይዞታ መጠቀሚያ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተርና ካርታ አዉጥቶበት ግብር እየከፈለበት እየተገለገለ እንደሚገኝ የአመልካች ምስክሮች በአንድ ቃል ከመመስከራቸዉም በላይ የሰነድ ማስረጃዎች ተያይዘዉ ቀርበዋል፡፡ ተጠሪ ዉል ተገባ ከምትለዉ ጊዜ በፊት እንኳ ይዞታዋ መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ ይሁን ዉል አያይዛ አላቀረበችም፡፡ የተጠሪ ምስክሮች ዉል ስለመኖሩም ሆነ ዉሉ ላይ በምስክርነት ስለመፈረማቸዉ አልመሰከሩም፡፡ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶች በይዞታ ማረጋገጫ ላይ የተሰጠበት ጊዜን የሚገልጸዉ ዓመተ ምህረት የማይነበብ ከሆነ ኦርጅናል ሰነዱ በአመልካች እጅ ስለሚገኝ በማስቀረብ ወይም የሰጠዉን አካል በመጠየቅ ማረጋገጥ ሲችሉ ከረጅም ጊዜ በፊት መያዙ አልተረጋገጠም በማለት የወረዳዉን ፍ/ቤት ዉሳኔ በመሻር የሰጡት ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲሻር የሚጠይቅ ነዉ፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ክርክር ያስነሳዉን ይዞታ ከ14 ዓመት በላይ ለሆነ ጊዜ ይዘዉ፤ በስማቸዉ የይዞታ ማረጋገጫ አዉጥተዉበት እየተገለገሉ ባሉበት እና የይዞታ ማረጋገጫቸዉ በሕግ አግባብ ባልተሰረዘበት እንዲሁም ተጠሪ ባለይዞታ ስለመሆናቸዉ የሚያረጋግጥ የይዞታ ማረጋገጫ ባልቀረበበትና መጋቢት 09 ቀን 2006 ዓ.ም በተደረገ ዉል ለተወሰነ ጊዜ በዉል አሳልፈዉ ለአመልካች ስለመስጠታቸዉ የሚያረጋግጥ አግባብነት ያለዉ ማስረጃ ባልቀረበበት፤ በተለይም በዉሉ ላይ ምስክር ሆነዉ ፈረሙ የተባሉ ሰዎች ቀርበዉ ባልመሠከሩበት ሁኔታ በስር ይግባኝ ሰሚና ሰበር ሰሚ ችሎቶች የኮንትራት ስምምነት በስር ተከሳሾች መካከል አለ የሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ ስምምነቱ ፈርሶ አመልካች ክርክር ያስነሳዉን ይዞታ ለቅቆ እንዲያስረክብ መወሰናቸዉ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 1195፣ 1196 እና በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 40 ንብረት የማፍራትና ያለአግባብ ያለመፈናቀል መብት እንዲሁም ከማስረጃ ምዘና መርህ አንጻር ለማጣራት ሲባል ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪ ለሰበር አቤቱታዉ የሰጡት መልስ ይዘት በአጭሩ፡- ክርክር ያስነሳዉ የገጠር መሬት ይዞታ በስር ፍ/ቤት 1ኛ ተከሳሽ የነበረዉ የተጠሪ ባለቤት ከአባቱ በዉርስ ያገኘዉ ሲሆን አባቱ ሲሞት ለአካለመጠን ያልደረሰ በመሆኑ በአጎቱ አቶ አማሎ ላሊማ ከራሳቸዉ መሬት ጋር አስመዝግበዉ፤ የይዞታ ማረጋገጫ አሰርተዉ ግብር እየገበሩ የነበረ መሆኑ እና በሥራ ምክንያት ተጠሪና ባለቤታቸዉ በአካባቢዉ ስላልነበሩ ባለቤታቸዉ ደብቆ ይዞታዉን ለአመልካች በኮንትራት በ2006 ዓ.ም መስጠቱን በሰዉና በሰነድ ማስረጃዎች ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ይዞታዉን ከ14 ዓመት በፊት የያዘዉ መሆኑን ቢገልጽም ይዞታዉ ወደ አመልካች

እስኪዛወር ድረስ በምን መልኩ ይዞት እንደነበረ ማስረዳት አልቻለም፡፡ የአመልካች የይዞታ ማረጋገጫ በስማቸዉ ያወጡቱ ከ14 ዓመት በፊት ጀምሮ ሳይሆን ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ እንደሆነ ነዉ፡፡ የግብር ካርኒዉም ከዚህ የተለዩ አይደለም፡፡ ይህም ከ2006 ዓ.ም በኃላ መያዙንና የተጠሪን አባባል የሚያጠናክር ነዉ፡፡ አመልካች የይዞታ ማረጋገጫ የተሰጠበትን ጊዜ አስመልክቶ አሁን የሚያነሱት ክርክር በስር ከፍተኛ ፍ/ቤት በቀረቡ ጊዜ ያላቀረቡት በመሆኑ ተገቢነት የለዉም፡፡ የይዞታ ማረጋገጫ ሊስተባበል የሚችል እንጂ ፍጹም ባለመሆኑ የማጭበርበር ድርጊቱ ከተፈጸመ ከ3 ዓመት በኃላ በሕጋዊ መንገድ የተሰጠ አለመሆኑ ተረጋግጦ የተሰጠ ዉሳኔ በመሆኑ ሊጸና ይገባል፡፡ ይዞታዉ የተጠሪ የነበረ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ አልቀረበም የተባለዉን በተመለከተ በከፍተኛ ፍ/ቤት ተጨማሪ ማስረጃ ለማቅረብ ተፈቅዶላቸዉ ይዘታዉ በተጠሪ ባለቤት አጎት በአቶ አመሎ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ እና የተጠሪ ባለቤትም ከቤተሰብ አባላት አንዱ ሆኖ ተመዝግቦ የሚገኝ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በሁለት ሌሎች ወገኖች የተጠሪን ጥቅም የሚጎዳ ዉል ስለመኖሩ ተጠሪ በሰዉ ማስረጃ እንዳያስረዱ እና የዉልን ሰነድ ብቻ በማቅረብ እንዲያስረዱ የሚያስገድድ ሕግ በሌለበት ዉል መኖሩን በሰዉ ምስክር እንዳያስረዱ የሚከለክላቸዉ ባለመኖሩ ዉል መኖሩ በሰዉ ምስክሮች ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም በዉሳኔዉ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የህግ ስህተት ባለመኖሩ እንዲጸና በመጠየቅ ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ሐምሌ 29 ቀን 2016 ዓ.ም የተዘጋጀ 2 ገጽ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸዉን በሚያጠናክር መልኩ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን እኛም አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡ የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር መርምረን እንደተረዳነዉ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሻዉ ጭብጥ፡- ክርክር ያስነሳዉን ይዞታ አመልካች ከ14 ዓመት በላይ ለሆነ ጊዜ ይዘዉ፤ በስማቸዉ የይዞታ ማረጋገጫ አዉጥተዉበት እየተገለገሉ ባሉበት እና የይዞታ ማረጋገጫቸዉ በሕግ አግባብ ባልተሰረዘበት እንዲሁም ተጠሪ ባለይዞታ ስለመሆናቸዉ የሚያረጋግጥ የይዞታ ማረጋገጫ ባልቀረበበትና መጋቢት 09 ቀን 2006 ዓ.ም በተደረገ ዉል ለተወሰነ ጊዜ በዉል አሳልፈዉ ለአመልካች ስለመስጠታቸዉ የሚያረጋግጥ አግባብነት ያለዉ ማስረጃ ባልቀረበበት፤ በተለይም በዉሉ ላይ ምስክር ሆነዉ ፈረሙ የተባሉ ሰዎች ቀርበዉ ባልመሠከሩበት ሁኔታ በስር ይግባኝ ሰሚና ሰበር ሰሚ ችሎቶች የኮንትራት ስምምነት በስር ተከሳሾች መካከል አለ የሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ ስምምነቱ ፈርሶ አመልካች ክርክር ያስነሳዉን ይዞታ ለቅቀ እንዲያስረክብ መወሰኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 1195፣ 1196 እና በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 40 ንብረት የማፍራትና ያለአግባብ ያለመፈናቀል መብት እንዲሁም ከማስረጃ ምዘና መርህ አንጻር ተገቢ ነዉ? ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነዉ፡፡

በመሠረቱ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1195(1) የማይንቀሳቀስ ንብረት የባለይዞታነት ወይም የባለቤትነት ምስክር የተሰጠዉ ሰዉ የዚሁ ንብረት ባለሀብት ሆኖ እንደሚቆጠር የሚደነግግ ሲሆን ይህም የማይንቀሳቀስ ንብረት

የባለሃብትነት ምስክር ወረቀት የተሰጠዉ ሰዉ የንብረቱ ባለሁብት ወይም ባለይዞታ እንደሆነ ሕጉ ግምት የሚወስድ መሆኑን ነዉ፡፡ ሆኖም ይህ የሕጉ ግምት ሊስተባበል የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1196 ድንጋጌ የሚያሳይ በመሆኑ አንድ ንብረት ወይም ይዞታ በአንድ ሰዉ ስም ስለመመዝገቡ በአስተዳደር መስሪያ ቤት ታዉቆለት የምስክር ወረቀት እስከተሰጠዉ ድረስ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1195(1) የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ በመመልከት የተወሰደዉን የባለይዞታነት ግምት ማስተባበል የሚቻለዉ ማስረጃዉ የተገኘዉ ከሕግ አግባብ ዉጭ በሆነ ሁኔታ መሆኑን በማስረዳት መሆኑን ነዉ፡፡ በተለይ ፈራሽ በሆነ ዉል ወይም በሕግ ፊት በማይረጋ ዉል መነሻነት በተላለፈለት ይዞታ ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ተሰጥቶታል የሚል ወገን የይዞታ ማረጋገጫዉ የተሰጠዉ በዚህ ዉል መነሻነት መሆኑን ወይም የይዞታዉ ማረጋገጫዉ ከመሰጠቱ በፊት የጸና የይዞታ መብት የነበረዉ መሆኑን ጭምር ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 183001 እና በሌሎች መዛግብት የሕግ ግምቱን ማስተባበል የሚቻለዉ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ ከሕግ አግባብ ዉጭ በሆነ ሁኔታ የተሰጠ መሆኑን በማስረዳት እንደሆነ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ግራ ቀኙን ያከራከረዉ የገጠር መሬት ይዞታ የአመልካች መሆኑን የሚያረጋግጥ ከሚመለከተዉ የአስተዳደር አካል የተሰጠ የማሳ መለያ ቁጥሩ 07-04-03-016-00498 የይዞታዉ ስፋት 0.66 ሄክታር መሆኑን የሚያመለክት የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በስር ፍ/ቤት መቅረቡ አከራካሪ አይደለም፡፡ ይህ የይዞታ ማረጋገጫ በ2000 ዓ.ም ወይም በ2010 ዓ.ም ለአመልካች መሰጡቱ የባለይዞታነት ግምቱ ላይ የሚያመጣዉ ለዉጥ የለም፡፡ ተጠሪ የዉል ሰነድ ሳያቀርቡ ዉል እንዲፈርስላቸዉ ያቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄ አመልካች ዉል አለመኖሩንና በዉል መነሻነትም ይዞታዉን አለመያዙን በግልጽ ክዶ የተከራከረ እንደመሆኑ መጠን አመልካች ይህን የባለይዞታነት ግምት ለማስተባበል ክርክር ያስነሳዉ ይዞታ የራሳቸዉ ይዞታ የነበረ መሆኑን የሚያረጋግጥ ወይም በዉሉ መነሻነት የይዞታ ማረጋገጫ ደብተሩን ስለማግኘቱ የሚያስረዳ በቂ ማስረጃ በማቅረብ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተሩን አሰጣጥ ሕጋዊነት ማስተባበል ይጠበቅባቸዋል፡፡

ከዚህ አንጻር ተጠሪ ክርክር ያስነሳዉ ይዞታ የተጠሪና ባለቤታቸዉ መሆኑን የሚያረጋግጥ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር አላቀረቡም፡፡ በስር ከፍተኛ ፍ/ቤት በተጨማሪ ማስረጃነት አቀርቡ የተባለዉም ቢሆን የተጠሪ ባለቤት አጎት ሰነድ እንጂ የባልና ሚስቱ ወይም የአንዳቸዉ መሆኑን የሚያረጋግጥ ካለመሆኑም በላይ ክርክር ያስነሳዉን ይዞታ የሚመለከትና ለተጠሪ የመክሰስ መብት የሚሰጥ መሆኑን የሚያሳይ አይደለም፡፡ የሰዉ ምስክሮችም ቃል ቢሆን የአመልካች ያቀረበዉ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር የሚሰጠዉን የባለይዞታነት ግምት ሊያስተባብል የሚችል አይደለም፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪ ክርክር ያስነሳዉ ይዞታ በአመልካች እጅ ሊገባ የቻለዉ ፈራሽ ወይም ሕገ-ወጥ ዉል መነሻነት ካሉም የዉሉን መደረግ ሰነዱን በማቅረብ ወይም ሰነዱ ጠፍቶ ከሆነ ወይም ተጠሪ ሊያገኙት

ያልቻሉ ከሆነ ዉሉ ሲደረግ የነበሩትን ምስክሮች በማስመስከር ወይም በቃል የተደረገ ከሆነም ይህንኑ በቀጥታ የሚያዉቁትን ምስክሮች በማቅረብ በበቂ ሁኔታ ሊያስረዱ ወይም ለአመልካች የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር የተሰጠዉ በዚሁ ዉል መነሻነት መብት ተላልፎለት መሆኑን ማስረዳት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህን አስመልክቶ ተጠሪ ለአመልካች የይዞታ ማረጋገጫ የተሰጣቸዉ የባለይዞታነት መብቱ በዉሉ መነሻነት ተላልፎለት መሆኑን የሚያስረዳ ምንም ዓይነት ማስረጃ አላቀረቡም፡፡ እንዲሁም ዉል መደረጉን ያዉቃሉ የተባሉ ሰዎችም ቢሆኑ በዉሉ ሰነድ ላይ በምስክርነት ፈረምን የሚሉ ሳይሆኑ መጋቢት 07 ቀን 2006 ዓ.ም የተደረገ ዉል መኖሩን እናዉቃለን፤ በምስክርነት ግን በዉሉ ላይ አልፈረምን ከማለት ባለፈ በዉሉ ላይ በምስክርነት ማን እንደፈረመ ያልገለጹ በምን ምክንያት እንዳወቁ ያልመሠከሩ ከመሆናቸዉ አንጻር ይግባኝ ሰሚዉ ፍ/ቤት ዉል አለ የሚል መደምደሚያ ላይ መድረሱ ተገቢ አይደለም፡፡ ተጠሪ ይዞታቸዉ ያለአግባብ ተይዞባቸዉ ከሆነ ይዞታቸዉ መሆኑን አግባብነት ባለዉ ማስረጃ በማስረዳት እንዲለቀቅላቸዉ መጠየቅ እንጂ ከጅምሩ የሌለን ዉል በማስፈረስ ሰበብ ባለይዞታነት ግምት ሊያገኙ አይገባም፡፡

ከላይ ከተገለጸዉ አንጻር የስር ይግባኝ ሰሚ ችሎቶች አመልካች ክርክር ያስነሳዉን ይዞታ ንብረት አፍርቶበትና የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ተሰጥቶት እየተገለገለበት ባለበት ሁኔታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 1196 አኳያ ከሕግና አሰራር ደንብ ዉጭ ለአመልካች የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር የተሰጠ መሆኑን አስመልክቶ ያቀረቡት መከራከሪያ በሌለበት፤ የተጠሪ ባለቤትንና አመልካችን የሚያስገድድ በሕግ አግባብ የተደረገ ዉል መኖሩ ባልተረጋገጠበት እና አመልካችም በዉል መነሻነት የይዞታ መብት የተላለፈለት መሆኑን ወይም የይዞታ ማረጋገጫ የተሰጠዉ መሆኑን የሚያረጋግጥ አግባብነት ያለዉ ማስረጃ ባልቀረበበት ሁኔታ ዉል አለ የሚል መደምደሚያ ላይ ደርሰዉ የወረዳዉን ፍ/ቤት ዉሳኔ በመሻር ዉሉ እንዲፈርስ የሰጡት ዉሳኔ መሠረታዊ የማስረጃ ምዘና መርህ ጥሰት የተፈጸመበት፤ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1195፣ 1196 ድንጋጌዎችንና ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 183001 እና በሌሎች መዛግብት የሰጠዉን አስገዳጅ ትርጉም ያላገናዘበ እንዲሁም አመልካችን ከይዞታዉና ንብረቱ ያለአግባብ ያፈናቀለና የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 40(4) ድንጋጌን የጣሰ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሀ እና ሸ) እንዲሁም አንቀጽ 10(1/ሐ) አንጻር መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በበንሳ አካባቢ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 05613 መስከረም 10 ቀን 2014 ዓ.ም ተሰጥቶ በሲዳማ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 04246 ታሕሳስ 14 ቀን 2015 ዓ.ም በተሰጠ ዉሳኔ እና በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 04694 የካቲት 24 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት በተሰጠ ዉሳኔ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ዉሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

የጸናዉ ዉሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1/ለ) መሠረት ተሽሯል፡፡

2. የአርቤጎና መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 594/5 ሰኔ 22 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ ጸንቷል፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

መ/ዐ                    የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

የሰ/መ/ቁ/ 244742

ህዳር 26 ቀን 2017ዓ/ም

ዳኞች፡-እትመት አሰፋ

ደረጀ አያና

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

ብርሃኑ መንግስቱ

አመልካች፡- ፖል ሪየስ እና ልጆቹ (ኢትዮጵያ) ሊሚትድ

ተጠሪ፡- የጉምሩክ ኮሚሽን አዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ጉዳዩ ያልተከፈለ ቀረጥና ታክስ የሚመለከት ሲሆን ጉዳዩ የጀመረው አመልካች በተለያዩ ዲክላራሲዮን ቁጥሮች ቀረጥና ታክስ በመክፈል ያስገባቸውን እቃዎች ተጠሪ የድህረ እቃ አወጣጥ ኦዲት በማድረግ ቀሪ ያልተከፈለ ቀረጥና ታክስ ከቅጣት እና ወለድ ጋር እንዲከፍል ውሳኔ በመስጠቱ እና አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለተጠሪ አቤቱታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት ቅሬታ ቢያቀርብም ተቀባይነት ባለማግኘቱ ነው፡፡ አመልካች ለተጠሪ ያቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት ማጣቱን ተከትሎም ይግባኙን ለፌዴራል ታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ኮሚሽኑም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ በቀን 02/04/2013 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 96/1//ሀ//4/ እና /5/

እቃዎችን እስከ ጉምሩክ መግቢያ በር ድረስ ለማድረስ የተከፈለ የትራንስፖርት፣የመጫኛ፣የማራገፊያ፣የመንከባከቢያና የኢንሹራንስ ወጪ ለእቃዎቹ በተከፈለው ወይም በሚከፈለው ዋጋ ላይ መደመር እንዳለበት ሆኖም እቃዎቹ በአየር የተጓጓዙ እንደሆነ ለአየር ትራንስፖርት የተከፈለው 1/3ኛ ወጪ በእቃው ዋጋ ላይ እንደሚካተት መደንገጉን፣አመልካች በተለያዩ ዲክላራሲዮኖች በአየር ተጓጉዘው ወደ አገር ያስገባቸው እቃዎች ላይ ከአየር ማጓጓዣው በተጨማሪ ሌሎች ወጪዎችን 1/3ኛ ብቻ በእቃው ዋጋ ላይ በማካተት ቀረጥና ታክስ ሲከፍል መቆየቱን፣ እነዚህ ተጨማሪ ወጪዎች በእቃው ዋጋ ላይ 1/3ኛ ብቻ ሳይሆን ሙሉ በሙሉ ሊካተቱ እንደሚገባ በህጉ ላይ በግልጽ የተቀመጠ መሆኑን እና ይህ በአመልካች የተካደ አለመሆኑን፣ ሆኖም አመልካች የሚያነሳው ክርክር በወቅቱ የነበረውን አሰራር ተከትሎ የተስተናገደ በመሆኑ ወደ ኋላ ተመልሶ ልጠየቅ አይገባም በሚል መሆኑን፣ በአዋጁ አንቀጽ 121/1/ እና 122/1/ በተደነገገው መሰረት ባለስልጣኑ የጉምሩክ ስነ ስርአት አጠናቀው የተለቀቁ እቃዎችን ዴክላራሲዮን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የድህረ እቃ አወጣጥ ኦዲት ሊያደርግና ያልተከፈለ ቀረጥና ታክስ በማናቸውም ምክንያት እንዳለ የተደረሰበት እንደሆነ በአምስት አመታት ውስጥ ሊያስከፍል እንደሚችል መደንገጉን፣ በዚህም ምክንያት አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የሌለው መሆኑን፣ ተጠሪ በአመልካች ያልተከፈለ ቀረጥና ታክሱን ከነወለዱ እንዲከፍል መወሰኑ ተገቢ መሆኑን፣ ቅጣትን በተመለከተ ግን በወቅቱ አመልካች በነበረው የአሰራር ስርአት መሰረት ሲስተናገድ የቆየ በመሆኑና ተጠሪም በህጉ መሰረት እየሰራ ያለመሆኑን አውቆ በ2010 ዓ.ም በጻፈው ማስታወቂያ አሰራሩን ያስተካከለ በመሆኑ ከ2010 ዓ.ም በፊት ለነበሩ ጉዳዮች ቀረጥና ታክሱ ሳይከፈል የቀረው በአመልካች ምክንያት/ ጥፋት/ ነው ሊያስብል እንደማይችል፣ በመሆኑም አመልካች ከ2015-2017 እ.ኤ.አ በተለያዩ ዲክላራሲዮኖች በአየር ትራንስፖርት ወደ አገር ያስገባቸውን እቃዎች በተመከለተ ሳይከፈል የቀረውን ቀረጥና ታክስ እንዲሁም ወለድ ቅጣትን ሳይጨምር እንዲከፍል በማለት የተጠሪን ውሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ግራ ቀኙ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ጉዳዩን አከራክሮ በሰጠው ውሳኔ ለቀሪ ቀረጥና ታክስ ያለመከፈል ምክንያት የነበረው ተጠሪ መሆኑን በዚህም ምክንያት አመልካች ቅጣትና ወለድ የሚከፍልበት የህግ ምክንያት የሌለ መሆኑን ገልጾ አመልካች ላልተከፈለ ቀሪ ቀረጥና ታክስ ወለድ ሊከፍል አይገባም ሲል የታክስ ይግባኝ ኮሚሽኑን ውሳኔ አሻሽሏል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ በሰጠው ውሳኔ በእቃዎች ዋጋ ላይ ተደምረው ቀረጥ እና ታክስ ሊከፈልባቸው የሚገቡ ወጪዎች ባለመጨመራቸው ምክንያት መከፈል የሚገባው ቀረጥ እና ታክስ ሳይከፈል የቀረ መሆኑ መረጋገጡን፣ በወቅቱ በእቃው ዋጋ ላይ ተገልጸው ቀረጥ እና ታክሱ መከፈል

ሲገባው ባለመከፈሉ ይህ ገንዘብ ለመንግስት ገቢ ተደርጎ ቢሆን ከዚሁ ሊከፈል ከሚገባው ቀረጥ እና ታክስ ገንዘብ ሊሰጠው የሚችለው ጥቅም / Time value of money / ሳይገኝ በመቅረቱ ይህንኑ ሳይከፈል በመቅረቱ ወይም በመቆየቱ ደግሞ ተጠቃሚ የነበረ መሆኑ ግልጽ ስለመሆኑ፣ ይህ ከሆነ ደግሞ መከፈል ሲገባው ሳይከፈል በቀረው ገንዘብ ላይ ወለድ ሊከፈል የሚገባ መሆኑን በመጥቀስ የፌ/ከ/ፍ/ቤት አመልካች ወለድ ሊከፍል አይገባም ሲል የሰጠውን የውሳኔ ክፍል በመሻር የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን የሰጠውን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

የአሁን ሰበር ቅሬታ የቀረበውም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት ለማሳረም ነው፡፡ የሰበር ቅሬታውም በአጭሩ፡- ተጠሪ አዲስ አሰራር እስከገበረበት መጋቢት 13/2010 ዓ.ም ድረስ በአዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 86/1/ /ሀ/ መሰረት በአየር ትራንስፖርት ተጓጉዞ የገባ እቃን በአየር የተጓጓዘበትን የአየር ትራንስፖርት የተከፈለውን 1/3ኛውን በጉምሩክ ዋጋ ላይ ተጨምሮ የእቃው ቀረጥና ታክስ ሲከፈልበት የነበረ መሆኑን እና በዚሁ መሰረት አመልካች ቀረጥና ታክሱን ከፍሎ እቃውን ለገበያ ማቅረቡን፣ ተጠሪ ያወጣው አዲስ አሰራር ማስታወቂያውን ካወጣበት ጊዜ ጀምሮ ተፈጻሚ ሊሆን የሚገባ እንጂ ወደ ኋላ ተመልሶ ሊሰራ የማይገባ መሆኑን፣ በአዋጁ አንቀጽ 122/2/ መሰረት ታክስና ቀረጥ ሳይከፈል የታለፈው ወይንም ሳይከፈል የቀረው በዲክላራሲዮን አቅራቢው ስህተት ካልሆነ ወለድም ቅጣትን አይከፈልም በማለት መደንገጉን፣ አመልካች ለቀሪ ቀረጥና ታክስ ያለመከፈል ምክንያት አለመሆኑን ወይም ጥፋተኛ አለመሆኑ መረጋገጡን፣ በዚህም ምንያት አመልካች ወለድ ሊከፍል ይገባል በማለት የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን ጠቅሶ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ተሽሮ የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲጸናልኝ የሚል ነው፡፡

ተጠሪ ለሰበር ቅሬታው የሰጠው መልስ በአጭሩ፡- አመልካች ሳይከፈል ለዘገየው ቀረጥና ታክስ ወለድ እንዲከፍል የተወሰነው በመቀጫነት አለመሆኑን፣ በፌዴራል ታክስ አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 37/1/ ስር በታክስ መክፈያ ጊዜው ወይም ከዚያ በፊት ታክሱን ያልከፈለ ታክስ ከፋይ ታክሱን መክፈል ከነበረበት ቀን ጀምሮ ተከፍሎ እስካለቀ ድረስ ባልተከፈለው ክፍያ መጠን ወለድ መክፈል እንዳለበት የተደነገገ መሆኑን፣ ዲክላራሲዮን አቅራቢው ጥፋት የሌለበት ቢሆንም እንኳ ቅጣት አይቀጣም ማለት እንጂ ሳይከፈል ለቀረው ቀረጥና ታክስ ወለድ አይከፍልም ማለት እንደልሆነ ከአዋጁ አንቀጽ 122/3/ /4//5/ ድንጋጌዎች መረዳት የሚቻል መሆኑን ጠቅሶ የሰበር ቅሬታው ወደቅ ይደረግልኝ ብሏል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ ያቀረበ ሲሆን ክርክሩን አጠናክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለፀውን ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ፣ ከጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እና ቅሬታው ለሰበር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ነጥብ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተው መርምሮታል፡፡ከክርክሩ ሒደት

መገንዘብ የቻልነው ተጠሪ በአየር ትራንስፖርት ተጓጉዞ የገባ እቃን በተመለከተ ከአየር ማጓጓዧው በተጨማሪ ሌሎች ወጪዎችን 1/3ኛ ብቻ በእቃው ዋጋ ላይ በማካተት ቀረጥና ታክስ ሲያከፍል መቆየቱን፤ እነዚህ ተጨማሪ ወጪዎች በእቃው ዋጋ ላይ 1/3ኛ ብቻ ሳይሆን ሙሉ በሙሉ ሊካተቱ እንደሚገባ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 96/1//ሀ//4/ እና /5/ የሚያመለክት በመሆኑ የቀደመውን አሰራሩን በህጉ አግባብ በማስተካከል አመልካች በህጉ መሰረት ተገቢው ቀረጥና ታክስ ከተገቢው ወለድና ቅጣት ጋር እንዲከፍሉ ውሳኔ ያስተላለፈ መሆኑን፤ቅጣትን በተመለከተ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በደረሰው ክርክር በወቅቱ አመልካች በነበረው የአሰራር ስርአት መሰረት ሲስተናገድ የቆየ በመሆኑና ተጠሪም በህጉ መሰረት እየሰራ ያለመሆኑን አውቆ በ2010 ዓ.ም በጻፈው ማስታወቂያ አሰራሩን ያስተካከለ በመሆኑ ከ2010 ዓ.ም በፊት ለነበሩ ጉዳዮች ቀረጥና ታክሱ ሳይከፈል የቀረው በአመልካች ምክንያት/ ጥፋት/ ነው የሚባልበት አግባብ ባለመኖሩ አመልካች ቅጣት ሊከፍሉ አይገባም፤ተገቢውን ቀረጥና ታክስ ከወለድ ጋር ሊከፍል ይገባል በማለት መወሰኑን የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ያሳያል፡፡ ስለሆነም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚፈልገው የክርክሩ መሠረታዊ ጭብጥ ዲክላራሲዮን አቅራቢው ለቀረጥ እና ታክሱ ያለመከፈል ምክንያት ካልሆነ ሳይከፈል ለቀረው ቀረጥ እና ታክስ ቅጣት እንዳይከፍል ከማድረግ ባለፈ ወለድ የመክፈል ሀላፊነቱን ያስቀርበታል? ወይስ አያስቀርበትም? የሚለው ነው፡፡

የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 122(1)(2) ድንጋጌ ቀረጥና ታክስ በማናቸውም ምክንያት ያልተከፈለ ወይም ሊከፈል ከሚገባው ያነሰ መሆኑ በድሕረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት የተደረሰበት እንደሆነ ባለስልጣኑ ዲክላራሲዮን አቅራቢውን ያልተከፈለውን ወይም በልዩነት ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥ እና ታክስ ሳይከፈል ከቀረበት ቀን ጀምሮ በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሊያስከፍል ይችላል ሆኖም ድንጋጌ ለቀረጥ እና ታክሱ ያለመከፈል ወይም በማነስ መከፈል ምክንያት የሆነው ዲክላራሲዮን አቅራቢው የሆነ እንደሆነ ሳይከፈል በቀረው ቀረጥ እና ታክስ ላይ አሥር በመቶ ቅጣት እና የባንክ ወለድ ተጨምሮ ይከፈላል በማለት ይደነግጋል፡፡ የዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) ባለስልጣኑ ኦዲት የሚያደርግ መሆኑን በጽሑፍ ካሳወቀ በኋላ ዲክላራሲዮን አቅራቢው ያልተከፈለ ቀረጥ እና ታክስ መኖሩን ከገለጸ እና ለመክፈል ፈቃደኛ ከሆነ ከቀረጥ እና ታክሱ እና ወለዱ ክፍያ በስተቀር ቅጣት እንዳይጣልበት ባለስልጣኑ ሊወስን ይችላል በማለት ይደነግጋል፡፡ ከድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መገንዘብ እንደሚቻለው በድሕረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት የተደረሰበት ሊከፈል የሚገባው ወይም ሳይከፈል የቀረ ቀረጥ እና ታክስ መኖሩ ከተረጋገጠ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ቀረጥና ታክሱ ሳይከፈል ከቀረበት ቀን ጀምሮ በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ማስከፈል እንደሚችል፤ ዲክላራሲዮን አቅራቢው ለቀረጥ እና ታክሱ ያለመከፈል ወይም በማነስ መከፈል ምክንያት ካልሆነ ሳይከፈል ከቀረው ቀረጥ እና ታክስ እና ወለዱ ክፍያ በስተቀር ቅጣት እንዳይጣልበት ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ሊወስን እንደሚችል ነው፡፡

በኢትዮጲያ በ 2016 ዓ.ም የታተመው ዐውደ ጥበባዊ የሕግ መዝገበ ቃላት ወለድ በብድር ለተወሰደ ወይም በባንክ ለተቀመጠ ገንዘብ ወይም በወቅቱ ላልተከፈለ ዕዳ የሚፈጸም ተጨማሪ ክፍያ ነው፤ የወለድ ጽንስ ሐሳብ ዓላማ አንድ ባለገንዘብ ገንዘቡን ለሌላ ሰው በመስጠቱ ምክንያት ለደረሰበት የአደጋ ተጋላጭነት ወይም ገንዘቡን ራሱ ለመጠቀም ያለውን ዕድል መስዋዕት በማድረጉ ምክንያት ገንዘቡን የተጠቀመበት ሰው ላገኘው ጥቅም ካሳ እንዲከፍለው ማድረግን ታሳቢ ያደረገ፤ በብድር በተገኘ ወይም እንዲቀመጥ በተሰጠ ገንዘብ በመጠቀም ለተገኘ ጥቅም ለባለገንዘቡ በመደበኛነት በተወሰነ ተመን የሚከፈል ገንዘብ፤ መከፈል በሚገባው ጊዜ ላልተከፈለ ገንዘብ በሕግ የተፈቀደ ወይም በተዋዋይ ወገኖች የተወሰነ፤ በዋናው ገንዘብ ላይ በመቶኛ የሚሰላ መካሻ ወይም ጥቅም ነው በሚል ተተርጉሚል፡፡ / ሰረዝ የተጨመረበት /

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 219003 በሰጠው ውሳኔ ወለድ በወቅቱ ሊከፈል ይገባው የነበረ ዋናው ገንዘብ ባለመከፈሉ ክፍያው ለዘገየበት የሚከፈል ክፍያ በመሆኑ በወቅቱ ባልተከፈለ ገንዘብ ላይ በባለመብቱ የሚጠየቅ የወለድ ጥያቄ ሊከፈል የሚገበው መሆኑን በመግለጽ በየትኛውም እርከን ላይ ለሚገኙ ፍርድ ቤቶች አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

በያዝነው ጉዳይ የአሁን አመልካች ለቀረጥ እና ታክሱ አለመከፈል ምክንያት ባለመሆናቸው ከቅጣት ነጻ ተደርገዋል፡፡ ሆኖም ተጠሪ በራሱ ችግር ምክንያት ቢሆንም በወቅቱ ሊከፈል ይገባው የነበረ ገንዘብ ያልተከፈለው እና ገንዘቡ በአመልካች እጅ የቆየ በመሆኑ አመልካች በወቅቱ ለተጠሪ ባልተከፈለው እና በእጃቸው ለቆየው ገንዘብ ለተጠሪ ሕጋዊ ወለድ የመክፈል ግዴታ አለባቸው፡፡ይህም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይባኝ ሰሚ ችሎት በወቅቱ አመልካች በነበረው የአሰራር ስርአት መሰረት ሲስተናገድ የቆየ በመሆኑና ተጠሪም በህጉ መሰረት እየሰራ ያለመሆኑን አውቆ በ2010 ዓ.ም በጻፈው ማስታወቂያ አሰራሩን ያስተካከለ በመሆኑ ከ2010 ዓ.ም በፊት ለነበሩ ጉዳዮች ቀረጥና ታክሱ ሳይከፈል የቀረው በአመልካች ምክንያት/ ጥፋት/ ነው የሚባልበት አግባብ ባለመኖሩ አመልካች ቅጣት ሊከፍሉ አይገባም፤ነገር ግን ተገቢውን ቀረጥና ታክስ ከተገቢው ወለድ ጋር ሊከፍሉ ይገባል በማለት የደረሰበት መደምደሚያ ከላይ የተመለከቱትን አስገዳጅ የህግ ትርጉሞች መሰረት ያደረገ፤መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ውሳኔ**

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.221964 በ26/04/2015 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስነስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9(1)(ለ) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ግራ ቀኙ በሰበር ክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ጉዳዩ ውሳኔ ስላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

**የሰ/መ/ቁ** 245352
**ህዳር** 27 **ቀን** 2017**ዓ/ም**

**ዳኞች**፡- ብርሃኑ አመነዉ

ገበየሁ ፈለቀ

በዕዉቀት በላይ

መላኩ ካሳዬ

ማርታ ተካ

**አመልካች**: - አቶ መኩሪያ መሶሬ አልቀረቡም

**ተጠሪ**፡- አቶ ታደሰ መሶሬ አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው የገጠር መሬት ይዞታን የተመለከተ ጉዳይ ሲሆን የተጀመረው በጠምባሮ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍ/ቤት አመልካች ተከሳሽ ሲሆኑ ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ ነበሩ፡፡ የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ በደቡብ ብ/ብ/ሕዝቦች ክልል በከምባታ ጠምባሮ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሀደሮ ምድብ ችሎት በመ/ቁ 02268 ጥር 26 ቀን 2015 ዓ.ም የወረዳዉን ፍ/ቤት በመሻር የሰጠዉና በየደረጃዉ ባሉ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ችሎቶች በተሰጠ ትዕዛዝ የጸናዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በሚል ነዉ፡፡

ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ:- አመልካች በአደራ ዉል የሰጠሁትን የገጠር እርሻ መሬት ይዞታ እንዲለቅና የራሱ ባልሆነ ይዞታ ላይ በአመልካች ስም የተሠራዉ የይዞታ ማረጋገጫ እንዲሰረዝ የሚጠይቅ ነዉ፡፡

አመልካች በበኩላቸዉ የገጠር መሬት ባለይዞታነት ማረጋገጫ ደብተር በመጀመሪያ ዙር በ1998 ዓ.ም ተሰጥቷቸዉ ለተከታታይ 17 ዓመታት ግብር እየገበሩበት የሚገኙበት ይዞታቸዉ ከመሆኑም በላይ ተጠሪ ነሐሴ 22 ቀን 1982 ዓ.ም በተደረገ የአደራ ዉል መስርተናል በማለት በሀሰት የተዘጋጀ ሰነድ ያቀረበ በመሆኑ በፎረንሲክ እንዲመረመርና ክሱ ዉድቅ እንዲደረግ በመጠየቅ ተከራክሯል፡፡

የጠምባሮ ወረዳ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ፤ ከወረዳዉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ይዞታዉ የማን እንደሆነ ተጣርቶ እንዲቀርብለት ካደረገ በኃላ መርምሮ፡- ክርክር ያስነሳዉን ይዞታ ተጠሪ ለአመልካች በአደራ መስጠቱን አለማረጋገጡን፤ ይልቁንም ይዞታዉ የአመልካች ሆኖ በስሙ የይዞታ ማረጋገጫ ያገኘበት በመሆኑ ይዞታዉን ለተጠሪ ለቅቆ ሊያስረክብ አይገባም እንዲሁም ለአመልካች የተሰጠዉ የይዞታ ማረጋገጫ ሊሰረዝ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝተዉ ተጠሪ ባቀረቡት ይግባኝ መነሻነት ጉዳዩን የተመለከተዉ የከምባታ ጠምባሮ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ መርምሮ ምንም እንኳ በቂ የፊርማ ናሙና ባለመገኘቱ አደራ ዉል በተባለዉ ላይ ያለዉ ፊርማ የአመልካች መሆን አለመሆኑ በፎረንሲክ ሊመረመር ባይችልም የተጠሪ ምስክሮች በ1968 ዓ.ም ክርክር ያስነሳዉን ይዞታ ተጠሪ መመራቱንና በ1982 ዓ.ም በሥራ ምክንያት ወደ ሌላ ቦታ ሲዛወር ለአመልካች በአደራ ሰጥቶ መሄዱን፤ በይዞታዉ ላይ ባሉት ባህር ዛፎች ምክንያት ተጠሪ ከሌላ ሰዉ ጋር ተከራክሮ በወረዳ ፍ/ቤት ለአመልካች ባህር ዛፉ የተፈረደለት መሆኑን ማስረዳቱን፤ አመልካች በበኩሉ የአደራ ዉል በግራ ቀኙ መካከል አለመኖሩን አለማስረዳቱን በመግለጽ በግራ ቀኙ መካከል ነሐሴ 22 ቀን 1982 ዓ.ም በተደረገ የአደራ ዉል መነሻነት የያዘዉ ይዞታ መሆኑን ተጠሪ ያስረዳ በመሆኑ ይዞታዉን ለተጠሪ እንዲያስረክብ እንዲሁም ለአመልካች የተሰጠዉ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲሰረዝ በማለት የወረዳዉን ፍ/ቤት ዉሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝቶ በየደረጃዉ ላሉት ለደቡብ ብ/ብ/ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቅሬታ ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘት፡- ተጠሪ ክርክር ያስነሳዉ መሬት ባለይዞታ መሆኑን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት በሌለበትና በስሙ ግብር የከፈለበት የግብር ደረሰኝ ባላቀረበበት ሁኔታ ባለይዞታ ሊሆን ስለማይችል መሬቱን በአደራ ሊሰጥ የሚችልበት የህግ አግባብ የለም፡፡ ነሐሴ 22 ቀን 1982 ዓ.ም በጽሁፍ ተደረገ የተባለዉ የአደራ ዉል በብዕር የተፈረመ ሲሆን አመልካች በብዕር መፈረም የማይችል በመሆኑ የፊርማ ናሙና ባለመገኘቱ በፎረንሲክ ሊመረመር ባይችልም የተጠሪ ምስክሮች አመልካች የፈረመዉ በጣት አሻራ ነዉ በሚል ከሰነዱ በተቃራኒ መስክረዋል፡፡ ይህም የአደራ ዉል ሰነድ የተባለዉ በሀሰት መዘጋጀቱን የሚያረጋግጥ ነዉ፡፡ ስለሆነም የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የተወሰኑ ምስክሮች ቃል ላይ በመመስረት ተጠሪ ባቀረበዉ ክስ መሠረት እንኳ ለ42 ኣመታት ሳይጠቀምበት ትቶት በቆየዉ ይዞታ ላይ

የሀሰት የአደራ ዉል አዘጋጅቶ በማቅረቡ ብቻ ይዞታዉ የተጠሪ ነዉ በማለት የወረዳዉን ፍ/ቤት ዉሳኔ መሻሩ ተገቢ አይደለም፡፡

የወረዳዉ ፍ/ቤት ከወረዳዉ ግብርና ጽ/ቤት ሕጋዊ ባለይዞታ ማን እንደሆነ ማስረጃ እንዲቀርብ በሰጠዉ ትዕዛዝ መሠረት ጽ/ቤቱ ከ1997 ዓ.ም በፊት ጀምሮ በስሙ ይዞ የሚገብርበት ይዞታ መሆኑ ተረጋግጦ በ1998 ዓ.ም የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ለአመልካች መሰጠቱን ከመረጃ ቋት በማረጋገጥ ገልጽዋል፡፡ አመልካች ይዞታዉን በሕገ-ወጥ መንገድ ወይም በአደራ ዉል መነሻነት ያለመያዙ ተረጋግጦ በወረዳ ፍ/ቤት የተሰጠዉን ዉሳኔ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት መሻሩም ሆነ በየደረጃዉ ያሉት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ችሎቶች ዉሳኔዉን ማጽናታቸዉ ተገቢ ባለመሆኑ እንዲሻር የሚጠይቅ ነዉ፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የወረዳዉ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር በማስረጃ በማጣራት በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተደረገ የመሬት ይዞታ አደራ ዉል አለመኖሩን፤ አመልካች አከራካሪዉን ይዞታ ከ1982 ዓ.ም ጀምሮ በመያዝ በስሙ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር አዉጥቶበት እና ግብር እየገበረ ሲጠቀምበት የቆየ መሆኑን በማረጋገጥ አመልካች አከራካሪዉን ይዞታ ለተጠሪ ለቅቆ ሊያስረክበዉ አይገባም በማለት ወሰነ ሲሆን የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የቀረበዉን ማስረጃ በመመዘን የአደራ ዉል ተረጋግጧል አመልካች አከራካሪዉን ይዞታ ለተጠሪ ለቅቆ እንዲያስረክብ በማለት የስር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በመሻር ያሳለፈዉን ዉሳኔ በየደረጃዉ ያሉት ፍ/ቤቶች ያጸደቁበት አግባብ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 40(4) አንጻር ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በሰበር ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ ለሰበር አቤቱታዉ የሰጡት መልስ ይዘት በአጭሩ፡- ማስረጃን ለመመዘን ስልጣን የተሰጣቸዉ የስር ፍ/ቤቶች የማስረጃ ምዘና መርህን ተከትለዉ የሰነድ ማስረጃዎችንና ገለልተኛ የሰዉ ምስክሮችን ምስክርነት እንዲሁም በይታዉ ላይ የሚገኝ ባህር ዛፍ የካሳ ክፍያን አስመልክቶ በወረዳ ፍ/በት በመዝገብ ቁጥር ፍ/ክ/ቁ 357/97 ተጠሪ ተከራክሮ የረታበት ማስረጃ ቀርቦና ተመዝኖ የተሰጠ ዉሳኔ በመሆኑ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ጥሰት የለዉም፡፡ የሰዉ ምስክሮች ተጠሪ ይዞታዉን የተመሩትና በይዞታዉ ላይ ከሚገኙ ንብረቶች ጭምር በአደራ ለአመልካች የሰጠ መሆኑን ያስረዱ ሲሆን አመልካች ተጠሪ በሌለበት ይዞታዉን ከማስለካቱ ዉጪ በሕግ ጥበቃ ሊደረግለት በሚችል መልኩ ያገኘዉ ስለመሆኑ ፈጽሞ ያስረዳዉ የለም፡፡ ይዞታዉ በአመልካች ስም በተለካበት ወቅት ተጠሪ ለሥራ ወደ ሌላ አካባቢ ሄዶ የነበረ መሆኑ በስር ፍ/ቤት ተረጋግጧል፡፡ ይዞታዉን በጽሁፍ በተደረገ የአደራ ዉል መሠረት አመልካች ከተረከበ በኃላ ከይዞታዉ የሚገኘዉን ምርት እያካፈለ ለተጠሪ ይሰጥ የነበረ ሲሆን በተጠሪ ስም ይከፈል የነበረዉን ግብር የገጠር መሬት ይዞታ ወደ ሌላ ሰዉ የሚተላለፍበትን ስርዓት ሳይከተል በአመልካች ስም የተከፈለዉ ግብርም ሆነ የተሰጠዉ የይዞታ ማረጋገጫ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 47139 በሰጠዉ አስገዳጅ ትርጉም መሠረት የይዞታ

ማረጋገጫ ይዞ መገኘት ብቻዉን ባለቤት አድርጎ የማያስቆጥር በመሆኑ የአመልካች ክርክር ተገቢነት የለዉም፡፡ አመልካች የራሱ የሆነ የግል ይዞታና መሬት ያለዉ በመሆኑና እንዲለቅ የተወሰነዉ የተጠሪን ይዞታ በመሆኑ የሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 40(4) ድንጋጌ ጥሰት አልተፈጸመም፡፡ ስለሆነም የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የወረዳዉን ፍ/ቤት በመሻር የሰጠዉና በየደረጃዉ ባሉት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ችሎቶች የጸናዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ባለመሆኑ እንዲጸና የሚጠይቅ ነዉ፡፡

አመልካች ነሐሴ 17 ቀን 2016 ዓ.ም የተዘጋጀ 4 ገጽ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸዉን በሚያጠናክር መልኩ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን እኛም አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡ የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር መርምረን እንደተረዳነዉ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሻዉ ጭብጥ፡- የወረዳዉ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር በማስረጃ በማጣራት በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተደረገ የመሬት ይዞታ አደራ ዉል አለመኖሩን፤ አመልካች አከራካሪዉን ይዞታ ከ1982 ዓ.ም ጀምሮ በመያዝ በስሙ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር አዉጥቶበት እና ግብር እየገበረ ሲጠቀምበት የቆየ መሆኑን በማረጋገጥ አመልካች አከራካሪዉን ይዞታ ለተጠሪ ለቅቆ ሊያስረክበዉ አይገባም በማለት የወሰነ ሲሆን የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የቀረበዉን ማስረጃ በመመዘን የአደራ ዉል ተረጋግጧል አመልካች አከራካሪዉን ይዞታ ለተጠሪ ለቅቆ እንዲያስረክብ በማለት የስር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በመሻር ያሳለፈዉን ዉሳኔ በየደረጃዉ ያሉት ፍ/ቤቶች ያጸደቁበት አግባብ ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 40(4) ድንጋጌ አንጻር መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነዉ፡፡

በመሠረቱ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 40(3) የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግስትና የሕዝብ ብቻ ነዉ፤ መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት ነዉ በማለት ሲደነግግ የዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ደግሞ የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች መሬት በነጻ የማግኘትና ከመሬታቸዉ ያለመፈናቀል መብታቸዉ የተከበረ ነዉ በማለት አስቀምጧል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ የሚቻለዉ አርሶ አደሮች በገጠር መሬት ላይ ያላቸዉ መብት በመሬት ይዞታቸዉ የመጠቀምና ከመሬታቸዉ ያለመፈናቀል ሲሆን የገጠር መሬት ሀብት ባለቤትነቱ የመንግስትና የሕዝብ በመሆኑ በሕግ ከተፈቀደዉ ዉጭ በማናቸዉም አግባብ ለ3ኛ ወገን ማስተላለፍ የማይቻል መሆኑን፤ እንዲሁም ለረጅም ዓመታት በመሬት ይዞታዉ የመጠቀም መብቱን በመተዉ ሌላ ቦታ ወይም ሌላ ሥራ ላይ ተሠማርቶ በመቆየቱ ሌላ አርሶአደር በመሬቱ ለረጅም ዓመታት ሲጠቀምና ግብር በስሙ ሲከፍል ቆይቶ የመሬት ልኬት ሲከናወንም በስሙ አስለክቶና የይዞታ ማረጋገጫ

አዉጥቶ ባለይዞታ የሆነን አርሶ አደር የተቋረጠ የመጠቀም መብትን መሠረት በማድረግ ከይዞታዉ ማፈናቀል የማይቻል መሆኑን ነዉ፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ በስር ፍ/ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠዉና አከራካሪ ያልሆነዉ ነጥብ አመልካች ክርክር ያስነሳዉን ይዞታ ከ1982 ዓ.ም ጀምሮ ቢቆጠር እንኳ ቢያንስ ከ34 ዓመት ላላነሰ ጊዜ በይዞታዉ እየተገለገለበት፤ በራሱ ስም ግብር እየከፈለና በክልሉ የመሬት ልኬት ማድረግ ሲጀመር በ1998 ዓ.ም ያለምንም ተቃዉሞ በስሙ አስለክቶና የይዞታ ማረጋገጫ አግኝቶበት እየተጠቀመ የሚገኝ መሆኑን ነዉ፡፡ በክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 110/1999 አንቀጽ 1(16) እና 6(3) መሰረት አመልካች የይዞታ ማረጋገጫ የተሰጠዉ መሆኑ ባለይዞታነቱን የሚያረጋግጥ ከመሆኑም በላይ በተግባርም ከ34 ዓመት ላላነሰ ጊዜ እየተገለገለበትና በስሙ ግብር እየከፈለ የሚገኝ እንደመሆኑ መጠን ባለይዞታነቱ አሻሚ አይደለም፡፡ ይህን ተመርኩዞ የወረዳዉ ፍ/ቤት አመልካች ይዞታዉን ሊለቅ አይገባም በማለት ወስኖ ነበር፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪ ክርክር ያስነሳዉ የመሬት ይዞታ እንዲለቀቅለት እየጠየቀ የሚገኘዉ ይዞታዉን በደርግ ዘመን መመራቱንና በ1982 ዓ.ም በሥራ ምክንያት አካባቢዉን ሲለቅ ወንድሙ ለሆነዉ አመልካች ነሐሴ 22 ቀን 1982 ዓ.ም በተደረገ የአደራ ዉል ሰጥቸዋለሁ በሚል ቢሆንም አመልካች የአደራ ዉሉን ያልፈረመበት መሆኑን፤ በተለይም ያልተማረ በመሆኑ በጣት አሻራ ካልሆነ በብዕር መፈረም እንደማይችልና በብዕር ተፈርሟል ተብሎ የቀረበዉ ሰነድ በሀሰት የተዘጋጀ ነዉ በማለት መከራከሩ እንደተጠበቀ ሆኖ በወቅቱ ሥራ ላይ የነበረዉ አዋጅ ቁጥር 31/1967 አንቀጽ 5 የገጠር መሬት ይዞታን በኪራይም ሆነ በማናቸዉም ሌላ መንገድ ማለትም ላልተወሰነ ጊዜ ወይም ለረጅም ጊዜ የመጠቀም መብት በሚያስተላልፍ የአደራ ዉል ጭምር ማስተላለፍን የሚከለክል በመሆኑ የአደራ ዉሉ ተደርጎም ቢሆን ሕገ-ወጥ ዉል ስለሚሆን ግራ ቀኙን የሚያስገድድ ስለማይሆን የአደራ ዉሉን መሠረት አድርጎ ተጠሪ ይዞታዉ እንዲለቀቅለት የሚያቀርበዉ ጥያቄ ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባም፡፡

ከላይ ከተገለጸዉ በተጨማሪ በተጠሪ በኩል የቀረቡት ምስክሮች በደርግ ዘመን ክርክር ያስነሳዉ ይዞታ ለተጠሪ ተመርቶ የነበረ መሆኑን መመስከራቸዉ መሬት የግል ሀብት እንደሆነና በመሬት ይዞታ የመጠቀም መብት ለረጅም ጊዜ ባለመጠቀም እንደማይቋረጥ ተቆጥሮ አመልካችን ከ34 ዓመት በኃላ ከይዞታዉ እንዲፈናቀል ለማድረግ የሚያስችል አይደለም፡፡ ተጠሪ ማስረዳት የሚጠበቅባቸዉ በደርግ ዘመን ይዞታዉን መመራታቸዉን ብቻ ሳይሆን በመሬት ይዞታ የመጠቀም መብታቸዉ ሳይቋረጥ እየተጠቀሙበት መቀጠላቸዉን ጭምር ነዉ፡፡ ይህን አስመልክቶ ተጠሪ በመሬቱ እየተጠቀሙበት የቀጠሉ ስለመሆናቸዉ የሚያስረዳ በስማቸዉ ግብር እየከፈሉ ስለመሆኑ ወይም እንደሌሎች የክልሉ አርሶ አደሮች የመሬት ልኬት ሲደርግ አስለክተዉ በስማቸዉ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር የተሰጣቸዉ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ አላቀረቡም፡፡ በሌላ ጉዳይ የባህር ዛፍ ካሳን በተመለከተ ከሌላ ሰዉ ጋር ተከራክረዉ መርታታቸዉን

በመግለጽ ያቀረቡት ክርክርም ቢሆን ከአመልካች ጋር ክርክር የተደረገበት ባለመሆኑ ለጉዳዩ አግባብነት የለዉም። ስለሆነም አመልካች ክርክር ያስነሳዉን ይዞታ ከ34 ዓመታት ላላነሰ ጊዜ በእጁ አድርጎ እየተገለገለበት፤ ግብር በስሙ እየከፈለበትና በክልሉ የገጠር መሬት ልኬት በተጀመረበት ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ በስሙ አስለክቶና የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ተሰጥቶት ኑሮዉን መስርቶበት ከሚገኝበት ይዞታዉ፤ ተጠሪ በደርግ ዘመን በምሪት ያገኘዉና በ1982 ዓ.ም በተደረገ የአደራ ዉል ለአመልካች የሰጠዉ ነዉ በሚል ምክንያት የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የወረዳዉን ፍ/ቤት ዉሳኔ በመሻር የሰጠዉ ዉሳኔም ሆነ በየደረጃዉ ያሉት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ችሎቶች ዉሳኔዉን በማጽናት የሰጡት ትዕዛዝ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 40(4) ድንጋጌን በሚቃረንና አመልካችን ከይዞታዉ በሚያፈናቀለ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ።

ሲጠቃለል የካምባታ ጠምባሮ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች ከ34 ዓመታት በላይ ለሆነ ጊዜ በይዞታዉ ስር አድርጎ እየተገለገለበትና በስሙ ግብር እየከፈለ ቆይቶ ያለምንም ተቃዉም በስሙ አስለክቶና የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ተሰጥቶት ኑሮዉን መስርቶ ከሚገኝበት ይዞታዉ በሚያፈናቅል መልኩ ይዞታዉን ለተጠሪ ለቅቆ እንዲያስረክብ በማለት የወረዳዉን ፍ/ቤት ዉሳኔ በመሻር የሰጠዉ ዉሳኔም ሆነ በየደረጃዉ ያሉት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤቶች ዉሳኔዉን በማጽናት የሰጡት ትዕዛዝ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 40(3 እና 4) ድንጋጌዎችን ያላገናዘበ እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሀ) እንዲሁም አንቀጽ 10(1/ሐ እና መ) አንጻር መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል። በመሆኑም የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል።

## ው ሳ ኔ

1. በከምባታ ጠምባሮ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 02268 ጥር 26 ቀን 2015 ዓ.ም ተሰጥቶ በደቡብ ብ/ብ/ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 21938 የካቲት 20 ቀን 2015 ዓ.ም በተሰጠ ትእዛዝ እና በክልሉ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 22010 መጋቢት 06 ቀን 2015 ዓ.ም በተሰጠ ትእዛዝ የጸናዉ ዉሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1/ለ) መሠረት ተሽሯል።
2. የጠምባሮ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 015028 ጥቅምት 17 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ ጸንቷል።
3. በጠምባሮ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 017338 የተጀመረዉ አፈጻጸም ለጊዜዉ ታግዶ እንዲቆይ የተሰጠዉ የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል። ይጻፍ።
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ።

መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል። ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ፋ/ዘ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት


የሰ/መ/ቁ 246211

ህዳር 27 ቀን 2017ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ገበየሁ ፈለቀ

በዕውቀት በላይ

መላኩ ካሳዬ

ማርታ ተካ

አመልካች፡- አቶ ኒአምን ጣሂር ሀሰን - ጠበቃ ጌቱ ሶሬሳ

ተጠሪ፡- አቶ ፈርሀን መሀመድ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የማይንቀሳቀስ ንብረትን ለመረከብ የቀረበ ክርክር ሲሆን የአመልካች የውጭ ሀገር ዜግነት ያላቸው ሆነው እያለ የሶማሌ ክልል ጅግጅጋ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የመዳኘት ስልጣን ሳይኖረው መወሰኑ እንዲሁም በየደረጃው ያሉት ፍርድ ቤቶችም ይህንኑ ውሳኔ ማጽናታቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በሚል የቀረበ የሰበር አቤቱታ የሚመለከት ነዉ፡፡

ተጠሪ ከሳሽ ሆነው በአሁኑ አመልካች ላይ ሶማሌ ክልል ጅግጅጋ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤት የመሰረቱት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- ንብረትነቱ የእኔና የወንድሜ የሆነውን በጅግጅጋ ከተማ ቀበሌ 06 የሚገኝ አራት ክፍል ቤቶች ያሉት 500ካ.ሜ ይዞታ የአሁኑ አመልካች የምንፈራቸውን ወታደሮች በመላክ ለቃችሁ

ካልወጣችሁ እንገላችኋለን በማለት በመዛት እና በመሳሪያ በማስፈራራት ተጠሪ ወደ ውጭ ሀገር እንድሄድ ካደረጉ በኃላ አመልካች ለስምንት አመት ይህንኑ ቤትና ይዞታዬ በማከራየት ኪራይ የሰበሰቡ በመሆኑ በኪራይ የሰበሰቡትን 912000(ዘጠኝ መቶ አስራ ሁለት ሺህ ብር) እንዲከፍሉኝ እንዲሁም ቤትና ይዞታውን እንዲያስረክቡኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁኑ አመልካች በሰጡት መልስ አመልካች የውጪ ሀገር ዜጋ ስለሆኑ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 5(ሐ) መሰረት የጅግጅጋ ከተማ አስተዳር ፍ/ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም፤ ተጠሪ ክስ ያቀረቡት ቤትና ንብረት ከወንድሜ ጋር በጋራ ያፈራነው ነው ቢሉም ንብረታቸው ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ አላቀረቡም እንዲሁም ቤቱንም ሆነ የኪራይ ገንዘብ ለመረከብ የሚያስችል የውክልና ስልጣን የሌላቸው በመሆኑ በሌላቸው መብት ክስ ሊያቀርቡ አይገባም የሚሉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን በማስቀደም በአማራጭ መልሳቸው አከራካሪው ቤትና ይዞታ በአሜሪካ በሚገኘው በሀሙድ ሙሀሙድ ስም የተመዘገበ ሲሆን አመልካች አሜሪካ በሚገኘው የኢትዮጵያ ኢምባሲ በተረጋገጠ ውክልና ተሰጥቶኝ በውክልና የሚያስተዳድረው ቤትና ይዞታ ሆኖ እያለ ተጠሪ የንብረቱ ባለቤት ከሆነው ግለሰብ የተሰጠው ውክልና ሳይኖር ይህንኑ ቤትና ይዞታ ለማስለቀቅም ሆነ ኪራይ እንዲከፈለው መጠየቅ ስለማይችል ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በሚል ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም በአመልካች በኩል የዳኝነት ስልጣን ጋር በተያያዘ የተነሳው መቃወሚያ ክርክሩ የንብረት ክርክር በመሆኑ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 80 ድንጋጌ መሰረት በጉዳዩ ላይ አከራክሮ የመወሰን ስልጣን አለኝ በሚል መቃወሚያውን ውድቅበማድረግ ክስ ሲሰማ አመልካች ባለመቅረቡ በሌለበት የተጠሪን ክርክርና የምስክሮች ቃል ሰምቶ እንዲሁም የመስክ ምልከታ ማድረጉንም ጠቅሶ እንደአጠቃላይ የቀረበው ክርክርና ማስረጃ መርምሮ በመዝገብ ቁጥር mmmJ/154/14፤በቀን 22/9/2014ዓ.ም ሲወስን አመልካች ተሰጠኝ የሚሉት ውክልና ሰነድ ተቀባይነት የለውም፤ ኪራይ እንዲከፈላቸው ተጠሪ የጠየቁት ዳኝነት ባለመቀበል፤ ተጠሪ አከራካሪው ቤትና ይዞታ ሊረከብ ይገባል በሚል ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዉ ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ በመዝገብ ቁጥር 05-2-16/2015፤ ህዳር 21 ቀን 2015ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ አጽንቷል፡፡ በመቀጠል አመልካች የሰበር አቤቱታቸዉን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበዉ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አላገኘሁበትም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ በመ/ቁ 05-1-196/15፤ ጥር 25 ቀን 2015ዓ.ም ወስኗል፡፡

አመልካች በቀን 24/08/2015ዓ/ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ ይዘትም አንዱ አመልካች የውጭ ሀገር ዜግነት ያለው በመሆኑ በበህገ መንግስቱ አንቀጽ 80/4 እና አዋጅ ቁጥር 1234/2013፤ አንቀጽ 5/ሐ/

መሰረት ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን ያለው የፌዴራል ፍርድ ቤት ሆኖ በውክልና ለፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠ ስልጣን የጅግጅጋ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤት የራሱ በማድረግ አመልካች ስልጣን በተመለከተ ያቀረበው መቃወሚያ አላግባብ ውድቅ በማድረግና ያለ ብይን በዝምታ በማለፍ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርኣት ሕግ ከሚያዘው መደበኛ የሙግት አመራር ውጪ ጉዳዩን በመምራት፤ የቀረበለትን ክስ የመፋለም ሆኖ እያለ የሁከት ክስ እንደሆነ አድርጎ በመውሰድና አንድ ላይ በመመርመር በማስረጃ ሳይጣራ ውሳኔ ማሳለፉም ሆነ የፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ህግን በጣሰ መልኩ ጉዳዩን በመምራት የክልሉ ሰበር አጣሪም ተገቢውን ማጣሪያ ሳያደርግ በስሩ ባሉት ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ውሳኔ ማጽናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት መፈፀማቸው ስለሚያሳይ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታቸዉን አቅርበዋል፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም የአመልካችን ሰበር አቤቱታ መርምሮ አመልካች በዜግነት አሜሪካዊ እንደሆኑ በመግለጽ የስር ጅግጅጋ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለመዳኘት ስልጣን እንደሌለው በመግለጽ ያቀረቡትን መከራከርያ ታልፎ ጉዳዩን በስረነገሩ ተመልክቶ ውሳኔ የሰጠበትን አግባብ ከፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 5(1/በ)፤ ኢ.ፌ.ድ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80/4 ስር ከተደነገገው ጋር ተገናዝቦ እንዲመረመር ተጠሪ መልስ እንዲሰጡ አዝዞ ተጠሪ በአድራሻቸው ሊገኙ ባለመቻላቸው ነሀሴ 4 ቀን 2016ዓ.ም በወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥሪ ተደርጎላቸው ስላልቀረቡ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

ከላይ አጠር ባለ መልኩ የተገለጸዉ የግራ ቀኙን ክርክርና በክልሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት የሚመለከት ሲሆን እኛም የጅግጅጋ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን የማየት ሥልጣን ያለው መሆን አለመሆኑን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነዉም ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሰረቱት ከወንድሜ ጋር በጋራ ያፈራነውን ቤት ከነይዞታው አመልካች ከህግ አግባብ ውጪ በሆነ መንገድ በመያዝ እያከራየ እየተጠቀመበት ስለሚገኝ የሰበሰበው ኪራይ ከፍሎ፤ አከራካሪው አራት ክፍል ያለው ቤት ከነይዞታው በፍርድ ኃይል ለመረከብ የቀረበ መሆኑን ከክርክሩ ተረድተናል፡፡ ክሱ በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን የቀረበዉ ለጅግጅጋ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነዉ፡፡ አመልካች በዜግነት አሜሪካዊ መሆናቸዉ ጠቅሰው ፍ/ቤቱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም በሚል መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን በተጠሪ በኩል አመልካች ዜግነታቸው አሜሪካዊ አደሉም በሚል ያቀረቡት ክርክር ስለመኖሩ የበታች ፍ/ቤቶች ውሳኔ አያሳይም፡፡ የጅግጅጋ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም አመልካች ከስልጣን ጋር በተያያዘ ያቀረቡት መቃወሚያ ውድቅ ያደረገበት ምክንያት በውሳኔው ላይ ካሰፈረው ለመረዳት እንደሚቻለው ክርክሩ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

የንብረት ክርክር በመሆኑ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 80 ድንጋጌ መሰረት በጉዳዩ ላይ አከራክሮ የመወሰን ስልጣን አለኝ በሚል ነው፡፡ የፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ሆነ የክልሉ ሰበር አጣሪ ችሎትም ተመሳሳይ አቋም በመያዝ ወስነዋል፡፡

እንደሚታወቀዉ ሥልጣንን በተመለከተ በተከራካሪዎች ክርክር ባይቀርብበትም በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 9(1) እና 231(1) (ለ) መሠረት ፍርድ ቤቶች በራሳቸው ተነሳሽነት አንስተው ሥልጣን የለኝም በማለት ክሱን መመለስ እንዳለባቸው የሚደነግግ ሲሆን የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 38452 ሰኔ 11 ቀን 2001 ዓ/ም በዋለው ችሎት አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ስር የፌደራል ፍርድ ቤት በፍትሐብሔር ጉዳዮች ላይ ስለሚኖረው ስልጣን አንቀጽ 5(1) ከፊደል ሀ እስከ ጀ ድረስ ባሉት በዝርዝር የተመለከቱ ሲሆን በዚሁ አንቀጽ 5(1) በ ስር የውጭ አገር ዜጋ ከሳሽ ወይም ተከሳሽ የሆነበት ጉዳይ የፌደራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ በግልጽ ይደነግጋል፡፡

ክርክሩ በተጀመረበት ሶማሌ ክልል ጅግጅጋ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካች ዜግነታቸው አሜሪካዊ ስለነበሩ ክርክሩ የውጪ ሀገር ዜጋ ተከሳሽ የሆኑበት በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 ቁጥር 5(1)(በ) መሠረት ጉዳዩ ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን ያለው የፌደራል ፍርድ ቤት ስለመሆኑ ያስገነዝባል፡፡ ይሁንና በኢትዮጵያ የፌደራል ሥርዓት መሠረት አድርጎ የተዋቀረው የዳኝነት ሥልጣን የፌደራል እና የክልል ፍርድ ቤቶች ካላቸው የጣምራነት ሥልጣን ባለፈ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 78(2) እና 80(4-6) የፌደራል ፍርድ ቤት በብቸኝነት ሥልጣኑ የሚመለከታቸውን ጉዳዮች የክልል ጠቅላይና ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች በውክልና እንዲመለከቱ ሥልጣን ሰጥቷል፡፡ ከዚህም የተነሳ የክልል ፍርድ ቤቶች በግዛታቸዉ ባሉ ሰዎች ወይም ንብረቶች ጋር በተያያዘ የሚነሳ የፌዴራል ጉዳይን በህገ መንግስት የተሰጣቸዉ (ስልጣን) በዉክልና በህገመንግስቱ አንቀጽ 78(2) መሰረት  የፌዴራል ፍርድ ቤት እስካልተደራጀ ወይም የዉክልና ስልጣን እስካልተነሳ ድረስ የመዳኘት ስልጣን ይኖራቸዋል፡፡ በተያዘዉ ጉዳይም ክሱ የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመረከብ የቀረበ ሲሆን ንብረቱ የሚገኘው በሶማሌ ክልል በመሆኑ በፍ/ብ/ስ/ስ/ ህግ ቁጥር 25(1/ሐ) እንደተመለከተዉ ክሱ መቅረብ የሚገባዉ ንብረቱ የሚገኝበት ግዛት ክልል ባለዉ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በዚህ ጉዳይም በክስ ማመልከቻቸው ከተጠቀሰው የሚያከራክረው ንብረት ግምት አንጻር ጉዳዩ የማየት ስልጣን ያለው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቢሆንም የማይንቀሳቀስ ንብረት የሚገኘው በሶማሌ ክልል

በመሆኑ በሕገ-መንግሥቱ በተሠጠው ውክልና መሠረት በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ ጉዳዩ የማየት ስልጣን ያለው የፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡

ሲጠቃለል የጅግጅጋ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤት አመልካች ዜግነት አሜሪካዊ ሆኖ እያለ በተጠሪ በኩል የማይንቀሳቀስ ንብረትን ለመረከብ የቀረበዉን ክስ በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን ተቀብሎ ለመዳኘት የሚያስችል የዳኝነት ሥልጣን ሳይኖረዉ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን ተቀብሎ መወሰኑም ሆነ የፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በይግባኝ ሲቀርብለት ሳያርም መቅረቱ እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 ቁጥር 10(1) (ሠ)ድንጋጌ መሠረት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች በህገ መንግስቱ በተሰጣቸው ስልጣን የፌደራል ጉዳይን አይቶ የሰጡትን የመጨረሻ ውሳኔ በሰበር አይቶ የማረም ሥልጣን የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት ሆኖ እያለ ፤ የሶማሌ ክልል ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት ጉዳዩን በሰበር የማየት ሥልጣን ሳይኖረው የፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ በማጽናት ትእዛዝ መስጠቱ ሊታረም የሚገባዉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የጅጅጋ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤት ጉዳዩ የማየት የዳኝነት ስልጣን ሳይኖረው በመዝገብ ቁጥር mmmJ/154/14፤በቀን 22/9/2014ዓ.ም አከራክሮ የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 05-2-16/2015፤ ህዳር 21 ቀን 2015ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ፤ እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 05-1-196/15፤ ጥር 25 ቀን 2015ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 ተሽሯል፡፡

2. የጅግጅጋ ከተማ አስተዳደር መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የውጭ ሀገር ዜጋ እና ኢትዮጵያዊ በሆኑ ተከራካሪዎች መካከል የሚቀርብ ክርክር አይቶ የመወሰን ስልጣን የለውም በማለት ተወስኗል፡፡
3. ይህ ዉሳኔ ሥልጣን ባለዉ ፍርድ ቤት ክስ ከማቅረብ አያግድም፡፡

4. በዚህ ችሎት የወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

5. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለክልሉ ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡ ሲጠይቁ ለግራ ቀኙም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

መ/ዐ

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 246690

ህዳር 26 ቀን 2017 ዓ.ም

**ዳኞች**፡-ሽመክት አሰፋ

አለማየሁ ሹናራ

ተናኜ ጥላሁን

ዋዚሞ ዋሲራ

ዘውዲቱ ታደሰ

አመልካች፡- አቶ አበባው ታደሰ - አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡- 1. የአ/ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት | አልቀረቡም

2. የአ/ብ/ክ/መ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

**ማስታወሻ**፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሚያዚያ 26 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 03-117980 በቀን 05/08/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ስለጠየቁ ነው፡፡ ጉዳዩ በክልል ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የተሰጠ አስተዳደራዊ ውሳኔን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁን አመልካች ለአ/ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ባቀረቡት ቅርታ መነሻ ሲሆን የቅሬታቸው ይዘትም ጉባኤው ጥር 25 ቀን 2010 ዓ.ም ባካሄደው መደበኛ ስብሰባ በየደረጃው ለሚገኙ ሰብሳቢ ዳኞች በተደረገው ደመወዝ ጭማሪ የስራ ሂደት አስተባባሪ እንደመሆኔ ተጨምሮልኝ ብር 13,702(አስራሶስት ሺ ሰባት መቶ ሁለት) ብር ሲከፈለኝ ቆይቶ ጉባኤው ሰኔ 12 ቀን 2012 ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ደመወዝ ጭማሪን አስልቶ ለጉባኤው ሲያቀርብ ሲከፈለኝ የቆየውን ደመወዜን በ1000 ብር የኃላፊነት አበል ነው በማለት በመቀነስ በጠቅላይ ፍ/ቤት ዳኛ መነሻ ደመወዝ ብር 12,702(አስራሁለት ሺ ሰባት መቶ ሁለት) ማስላቱ ተገቢ ስላልሆነ መነሻ ተደርጎ ሊሰላ የሚገባው ሲከፈለኝ በቆየው ደመወዝ ብር 13,702(አስራሶስት ሺ ሰባት መቶ ሁለት) ብር ላይ ነው በማለት ለ2ኛ ተጠሪ ቅሬታ አቅርበው 2ኛ ተጠሪ ጉባኤው ጥር 25 ቀን 2010 ዓ.ም የወሰነው ክፍያ የኃላፊነት ክፍያ እንጂ ደመወዝ ባለመሆኑ የአመልካች ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ አድርጎ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት የአሁኑን 1ኛ ተጠሪን በተጠሪነት በመጨመር ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበዉ ችሎቱ ግራ ቀኙን በመ/ቁጥር 03-104522 ላይ አከራክሮ በቀን 30/11/2013 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ ጉባኤዉ በአዋጅ ቁጥር 209/2006 መሰረት የዳኞችን እና የጉባኤ ተሿሚዎችን ደመወዝ ጥቅማጥቅም የመወሰን ሥልጣን ያለዉ አካል ነዉ፡፡ጉባኤዉ የሚሰጣቸዉ ዉሳኔዎች አግባብነት ለመከለስ በሕግ ሥልጣን የተሰጠዉ ሌላ አካል የለም፡፡በመሆኑም ጉባኤዉ በተለያዩ አስተዳደራዊ ጉዳዮች ሊይ የሚሰጠዉ ዉሳኔ የመጨረሻ እንደሆነ ይቆጠራል፡፡የኢ.ፌ.ድ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ለ) እና በተሻሻለዉ የአማራ ክልል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 223/2007 አንቀጽ 17 በግልጽ እንደሚደነግገዉ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበትን በክልል ጉዳዮች የተሰጠ የመጨረሻ ዉሳኔ የማረም በሰበር ችሎት የማየት ሥልጣን እንደሚኖረዉ ያስገነዝባል፡፡በዚህ ጉዳይ ዉሳኔ የሰጠዉ ጉባኤዉ ስለሆነ እና ዉሳኔዉም የመጨረሻ በመሆኑ የክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን

ማስ ታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

የማየት ሥልጣን ስላለዉ ተጠሪዎች ችሎቱ ስልጣን የለዉም ሲሉ ያቀረቡት ተቃዉሞ ተቀባይነት የለዉም ብሎ በይኗል፡፡

በመቀጠል ጉባኤዉ በቀን 25/05/2010 ዓ/ም የወሰነዉ ደመወዝ ነዉ ወይስ የኃላፊነት አበል የሚለዉን በመመርመር በጉባኤዉ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 209/2006 ላይ እና በሌሎች የዳኞች መተዳደሪያ ደንቦች ላይ የደመወዝ ትርጓሜ ስላልተሰጠ በክልል የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 253/2010 አንቀጽ 2/9 ሊይ የተሰጠዉን ትርጓሜ መዋስ ይገባል በማለት ጉዳዩን ከዚህ አንጻር መርምሯል፡፡በዚህ መሰረት ጉባኤዉ በቀን 25/05/2010 ዓ/ም ለሰብሳቢ ዳኞችና ለስራ ሂደት መሪዎች ክፍያ ሲወስን መጠኑን የወሰነዉ ሠራተኞች የሚያገኙትን መነሻ ደመወዝ መሠረት በማድረግ የደረጃ እና እርከን መስራቱን የጉባኤዉ ቃለ ጉባኤ ያሳያል፡፡ከፍ ሲሌ ከተመለከተዉ የደመወዝ ትርጓሜ አንጻር በክፍያዉ ላይ ጡረታ ሲቆረጥ መቆየቱ ሲታይ ጉባኤዉ የወሰነዉ ክፍያ ደመወዝ እንደሆነ ችልቱ ተገንዝቧል፡፡ስለሆነም ጉባኤዉ በቀን 25/05/2010 ዓ/ም ሰብሳቢ ዳኞችና የስራ ሂደት መሪዎች የወሰነዉ ክፍያ የኃላፊነት አበል ሳይሆን ደመወዝ በመሆኑና ዉሳኔዉ ፀንቶ ባለበት የዳኞችና የጉባኤ ተሿሚዎች ደመወዝ በተሻሻለ ጊዜ ለስሌቱ በመነሻነት ሊወሰድ የሚገባዉ አመልካች አስቀድሞ በሂደት መሪነታቸዉ ሲከፈላቸዉ የነበረዉ ደመወዝ ብር ሆኖ እያለ በመነሻ ደመወዝ መሰራቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ በማለት ጉባኤዉ በቀን 26/06/2013 ዓ/ም ያስተላለፈዉን ዉሳኔ በመሻር ጉባኤዉ ለሰብሳቢ ዳኞችና የሂደት መሪዎች የወሰነዉ ክፍያ ደመወዝ ነዉ ሲል ወስኗል፡፡

ተጠሪዎች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 214219 ይግባኝ አቤቱታቸውን ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም ተጠሪዎች ያቀረብነዉን መቃወሚያ ተቀብሎ አቤቱታዉን ዉድቅ ማድረግ ሲገባዉ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን ሳይኖረዉ የጉባኤዉን ዉሳኔ መሻሩ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ጉባኤዉ ፍርድ ቤቶችን እና ዳኞችን ለማስተዳደር በሕግ ሥልጣን የተሰጠዉ ሲሆን አከራካሪዉ ጉዳይ የደመወዝ ማሻሻያ እና የኃላፊነት አበል ክፍያ በተመለከተ የሰጠዉ ዉሳኔ በመሆኑ የክርክር አመራር ሂደትን ተከትሎ አከራክሮ የወሰነዉ አይደለም፡፡ በመሆኑም ዉሳኔዉ አስተዳደራዊ እንጂ በዳኝነት ነክ አግባብ ታይቶ የተወሰነ አይሆንም፡፡በመሆኑም የክልል ሰበር ችሎት ሥልጣን ሳይኖረዉ አስተዳራዊ ዉሳኔ በመመርመር የሰጠዉ ዉሳኔ በሰ/መ/ቁጥር 92546 ላይ የተሰጠዉን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሚቃረን በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ 1ኛ የአሁን ተጠሪ በጉዳዩ ሊይ የሰጠዉ ዉሳኔ በሌለበት ዉሳኔ የሰጠዉም ጉባኤዉ ሆኖ እያለ አመልካች 1ኛ ተጠሪን በተጠሪነት በመሰየም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

አቤቱታ ለክልል ሰበር ማቅረባቸዉ ተገቢ አይደለም በማለት፣ ችሎቱ 1ኛ ተጠሪን ከክርክሩ ዉጭ እንዲያደርግ የቀረበለትን ክርክር ምንም ምክንያት ሳይገልጽ 1ኛ ተጠሪን የክርክሩ አካል አድርጎ የሰጠዉ ዉሳኔ የ1ኛ ተጠሪን በኢ.ፌ.ድ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 37/1 ስር የተደነገገዉን ፍትህ የማግኘት መብት የሚቃረን ነው በማለት ጠይቀዋል፡፡

የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ  ችሎቱም መዝገቡን ከመረመረው በኋላ የክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ዳኝነታዊ ክለሳ የማድረግ ሥልጣን ጭምር እንዳለዉ በክልል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ላይ በልዩ ሁኔታ ያልተደነገገ በመሆኑ ጉባኤው የሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ በዳኝነታዊ ክለሳ ሥርዓት ከመታየቱ በፊት በስረ ነገሩ የክልል ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር ማየቱ በፌደራል ህገ መንግስት አንቀጽ 80/2 እና በክልል ሕገ መንግስት አንቀጽ 67 (2/ሀ) ላይ በተደነገገው መንፈስና ይዘት መሰረት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በክልላዊ ጉዳይ ላይ በጉባኤው የተሰጠውን አስተዳደራዊ ውሳኔ በዳኝነታዊ ክለሳ የማየት ሥልጣን እንዳለው የሚያስገነዝበውን ያላገናዘበ በመሆኑ ሥነ-ሥርዒታዊ ስላልሆነ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10(1/ሐ) መሰረት ሊታረም የሚገባው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው በማለት የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 03-104522 ላይ በቀን 30/11/2013 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት በመሻር አመልካች በጉባኤው የተሰጠ ውሳኔ በዳኝነታዊ ክለሳ እንዲታይ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት አቤቱታ ከማቅረብ ይህ ውሳኔ አያግዳቸዉም በማለት አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

አመልካች በጉባኤው በተሰጠው ውሳኔ የዳኝት ክለሳ እንዲታይ የመጠየቅ ስልጣን ተጠብቆ በተወሰነላቸው መብታቸው አግባብ ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 01-58677 የክልሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የካቲት  26 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ የዳኝነት ክለሳ እንዲካሄድበት ጠይቀው ፍ/ቤቱ ግራቀኙን አስቀርቦ መዝገቡን ከመረመረ በኋላ አመልካች በየጊዜው በሰብሳቢነት ደመወዝ ሲሻሻል የተጻፈላቸውን ልዩ ልዩ ደብዳቤዎች ፣ የስራ ሂደት ሆነው በጉባኤ ሲሾሙ የተጻፉ ደብዳቤዎች ፣ የክልሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ግንቦት 28 ቀን 2012 ዓ.ም ደመወዝ ማሻሻያ በሚል የተያዘው አጀንዳ የጥናት ሰነዱም በ80% የደመወዝ ማሻሻያ የሚለውን በመመልከት የአመልካች ቅሬታ የሚከፈለኝ ደመወዝ ነው በሚል ያቀረቡት አቤቱታ የሚለውን በመመልከት የአመልካች ቅሬታ ተገቢ ነው በማለት፣ የሀላፊነት አበል የሚው አገላለጽ የቃል አጠቃቀም እንደሆነ ግንቦት 28 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ በድጋሚ በመመልከት ደመወዝ ስለሆነ ውሳኔ እንዲሰጥ ይህን የዳኝነት ክለሳ ውሳኔ ሰጥተናል በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪዎች ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 117980 የይግባኝ አቤቱታቸውን አቅርበው የአ/ብ/ክ/መ/ ሰበር ሰሚ ችሎት መዝገቡን ከመረመረው በኋላ አመልካች ለቅሬታቸው መነሻ ያደረጉት በጥር 25 ቀን 2010 ዓ.ም የተሰጠው የጉባኤው ውሳኔ ለዳኞችና ለጉባኤው ተሿሚዎች ደመወዛቸውና የኃላፊነት አበላቸው መጠን በግልጽ ተለይቶ የተወሰነ ስለሆነ በየካቲት 26 ቀን 2013 ዓ.ም  2ኛ ተጠሪ ጉባኤው የተጠሪን ቅሬታ ውድቅ በማድረግ የተሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ በዳኝነት ክለሳ ሊታረም የሚገባው ስህተት ያልተፈጸመበት ሆኖ እያለ የስር የአ/ብ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት በዳኝነት ክለሳ የሚታረም ስህተት አለ በማለት  ለጉባኤው መመለሱ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት  አቅርበው ፤የአ/ብ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 01-58677 በቀን 29/11/2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት በዳንነት ክለሳ ስልጣኑ አይቶ የሰጠውን ውሳኔ በአብላጫ ድምጽ ሽሮታል፡፡

ቅሬታው የቀረበው የክልሉን ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ በመቃወም ሲሆን አመልካች በጥር 25/2010 በስራ ሂደት አስተባባሪነታች የተጨመረላቸው የደሞዝ ጭማሪ እንጂ የሀላፊነት አበል ያለመሆኑን በመግለጽና፤በግንቦት 28/2012 ደመወዝ ሲጨመር መነሻ መደረግ የሚገባው የስራ ሂደት አስተባባሪ ሲሆኑ በተጨመረው ላይ መሆን ነበረበት በማለት በዝርዝር ይደግፈኛል የሚሉትን ምክንያት አስቀምጠው ቅሬታ አቅርበዋል፡፡በዚህ ሰበር ችሎት የአመልካች ደሞዝ ከየካቲት 1/2010 ጀምሮ ወደብር 13702(አስራሶስት ሺ ሰባት መቶ ሁለት) አድጎላቸው  በዚሁ አግባብ ሲከፈላቸው ቆይቶ እያለ የክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ  ሰኔ28/2012 የዳኞችና የጉባኤ ተሸዋሚዎች ደሞዝ ሲወስን ጭማሪው በግዜው ሲከፈላቸው በነበረው ደሞዝ መሆን ሲገባው ከየካቲት 1/2010 በፊት ይከፈላቸው በነበረው ደሞዝ ይሁን ብሎ መወሰኑ ተገቢ አደለም በማለት እንደገና እንዲታይ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ የክልሉ ሰበር የመሻሩን አግባብነት ለማየት መዝገቡ ያስቀርባል ተብሎ ግራቀኙ መልስና የመልስ መልስ ተቀባብለዋል፡፡

እኛም የቀረበውን ክርክር፤በክልሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጡት ውሳኔዎች፤ በመዝገቡ የተያዘውን ጭብጥ ከህግ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡ አመልካች የክልሉ ሰበር በፍሬ ጉዳይና በማስረጃ ጉዳይ ገብቶ ውሳኔ ሰጠ የሚሉትን መከራከርያ በተመለከተ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤው በጥር25/2010 እና በግንቦት 12/2012 የሰጠውን ውሳኔ ምንነት ከህግ ጋር በማገናዘብ ተርጉሞ የሰጠበት ውሳኔ በመሆኑ በፍሬጉዳይና ማስረጃ ላይ ገብቶ አላግባብ ወሰነ የሚባል ሆኖ አላገኘነውም፡፡ አመልካች በጥር 25/2010 የስራ ሂደት ሀላፊ በመሆኔ የተጨመረልኝ ደሞዝ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ጭማሪ እንጂ የሀላፊነት ክፍያ አደለም፤የስራ ግብርና የጡረታ አበልም ሲቆረጥብኝ ቆይቷል ፤ስለዚህም በግንቦት28/2012 ለዳኛ ሁሉ ደሞዝ ሲጨመር ለጭማሪ በመነሻነት ሊያዝ የሚገባው የስራ ሂደት ሀላፊ በመሆኔ ከተጨመረው ጋር ከነበረኝ ብር 13702(አስራሶስት ሺ ሰበትመቶ ሁለት) እንጂ የ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ ደሞዝ ከሆነው ብር 12702(አስራ ሁለት ሺ ሰባት መቶ ሁለት) ሊሆን አይገባውም ይላሉ ። በተጠሪዎች በኩል ደግሞ የሰብሳቢ ዳኛም ሆነ የስራ ሂደት አስተባባሪ ጭማሪ የሀላፊነት ክፍያ እንጂ ደሞዝ አደለም፤ግብርና ጡረታ ያለአግባብ ተቀነሰ ከተባለ ይህን በህግ አግባብ ከሚጠይቁ በስተቀር የደሞዝ ጭማሪው የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ ደሞዝ መነሻ ተደርጎ መጨመሩ ምንም የህግ ስህተት የለበትም በማለት ይከራከራሉ፡፡

በግንቦት 28/2012 ለዳኞችና ለጉባኤ ተሽአሚዎች የደመዝ ጭማሪ በማድረግ ሲወሰን ለስራ ሂደት አስተባባሪ ለሁሉም ዳኛ ከተጨመረው ደሞዝ በተጨማሪ ለብቻ የስራ ሂደት አስተባባሪ በመሆናቸው ብር 2500(ሁለትሺ አምስት መቶ) እንደተጨመረና አመልካችም የዚሁ ተጠቃሚ እንደሆኑ መዝገቡ ያሳያል፡፡የስራ ሂደት አስተባባሪነት ደግሞ ቋሚ ሆኖ ላይቀጥል የሚችልና አስተባባሪነቱ ሲቀር ክፍያውም የሚቀር ነው፡፡ አመልካች ተጨመሩልኝ የሚሉዋቸው ሁለት እርከኖች አንዱ ሰብሳቢ ዳኛ ሲሆኑ የተጨመረ፤ሌላው ደግሞ አስተባባሪ በመሆናቸው የተጨመረ ነው፡፡

በመሰረቱ እርከን እየተባለ መጨመሩም ሆነ፤ ግብርና ጡረታ የተቆረጠበት መሁኑ ደሞዝ ነው ብለው አመልካች እንዲያስቡ ያረገ ቢሆንም፤የስራ ሂደት አስተባባሪነት ክፍያ የስራ ሂደት ማስተባበሩን አቁመው በዳኝነታቸው ብቻ በሚቀጥሉበት ግዜ ክፍያውም አብሮ የሚቀር ስለሆነና መሆንም ስለሚገባው፤ በሌላ በኩል የስራ ሂደት አስተባባሪ ተብለው ለዚሁ ለብቻው በጉባኤ የተወሰነው አበል እየተከፈላቸው መልሰው ደግሞ የስራ ሂደት አስተባባሪ ስሆን የተሰጠኝ ጭማሪ የደሞዝ ጭማሪ ስለሆነ አሁን የሚደረግ ጭማሪ ከሱ ላይ ተነስቶ ይጨመርልኝ ማለታቸው ያለአግባብ ተጠቃሚ ስለሚያረጋቸው፤ በጥር25/2010 የተደረገው ጭማሪ የሀላፊነት አበል ነው የሚለው ትርጉም ምክንያታዊና አሳማኝ ሆኖ ስላገኘነው፤ የክልሉ ሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት አደለም ብለን ከዚህ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

ማስ ታወሻ፡ - ይህ የ ሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነ ድ ለ ጥና ትና ምር ምር ሥራ ወይምለ ግንዛ ቤ እ ን ጂ

ለ ፍር ድ አ ፈ ጻ ጸ ምዓ ላ ማአ ያ ገ ለ ግል ም!

- የአ/ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 117980 በሚያዝያ 15/2015 የሰጠውን ውሳኔ በሰበር/ስ/ስ/መመርያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1)(ሀ) መሰረት አጽንተነዋል፡፡
- የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ ይቻቻሉ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መዝገብ ቁጥር 247466

ህዳር 27 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች ፡--ሸመክት አሰፋ

አለማየሁ ሹናራ

ተናኜ ጥላሁን

ዋዚሞ ዋሲራ

ዘዉዲቱ ታደሰ

አመልካች፡----- አቶ ገብረፃድቅ ገብረኪዳን ቀረቡ

ተጠሪ፡---------ፋና ብሮድካሲቲንግ ኮርፖሬት አክስዮን ማህበር ነ/ፈጅ መስፍን ተስፋዬ

መዝገቡ ከተዘጋ በኃላ የቀረበዉ አመልካች በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 208 መሰረት ስህተት ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ መሰረት ተደርጎ ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጠ፡፡

**ዉሳኔ**

አመልካች ያቀረቡትም ቀደም ሲል በተሰጠዉ ፍርድ ላይ ተፈፀመ ስህተት በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 208 መሰረት ይታረምልኝ ሲሉ የጠየቁትን ላይ ተጠሪ አስተያየት እንዲሰጥበት ተደርጎ ጉዳዩን ከሕጉ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ ተመርምሯል፡፡

አመልካች ባቀረቡት አቤቱታ ላይ በግራ ቀኛችን መካከል ያለዉ ኪራይ ዉል ፀንቶ የሚቆየዉ ለአንድ አመት ከስድስት ወር ሲሆን መጋዘኑን ለማስተካከል የሁለት ወራት ተቀናሽ ተደርጎ የአራት ወራት ይከፈል ተብሎ የተወሰነ ሲሆን ፍርድ ቤቱ በግራ ቀኛችን ያለዉ የኪራይ ዉል የአንድ አመት ከስድስት ወራት ስለመሆኑ ገልፆ እያለ ዉሉ የተደረገዉ ለአንድ አመት ብሎ መወሰኑ ስህተት ስለሆነ ያልተከፈለኝ ቀሪ የአንድ አመት ኪራይ ብር 3,450,000.00 (ሶስት

ሚሊዮን አራት መቶ አምሳ ሺህ ብር) ተጠሪ እንዲከፍለኝ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 208 መሰረት ታርሞ ይወሰንልኝ ሲሉ ጠይቋል ፡፡ተጠሪ በበኩሉ አስተያየት እንዲሰጡበት የተደረገ ሲሆን ያቀረቡት አስተያየትም አጠር ባለመልኩ ሲታይ፡-አመልካች በተጠሪ ላይ ተጨማሪ ገንዘብ እንዲከፈል በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 208 ያቀረቡት ጥያቄ የህጉን መንፈስ ያለተከተለ ሲሆን አመልካች እያነሱ ያለዉ ጥያቄ በፍርድ ቤት አፃፃፍ ስህተት ሳይሆን በእራሱ የአመልካች የአፃፃፍና የማስረዳት ዉስንነት እንደሆነ የሚታይ እንጂ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 208 መሰረት በቃል ወይም በቁጥር አጻጻፍ ስህተት ላይ ባልታሰበና ባለማስተዋል በፍርድ ቤት ዉሳኔ ላይ የተፈፀመ ስህተት ወይም ጉድለት በሌለበት ሁኔታ በፍርድ ቤት ዉሳኔ ላይ እንደተፈፀመ ስህተት አድርገዉ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 208 መሰረት እንዲታረም የጠየቁት ጥያቄ ተገቢነት የለዉም የሚል አስተያየት ሰጥቷል፡፡

እኛም የቀረበዉን የአመልካች አቤቱታ መርምረን እንዳየነዉ ሳይታሰብ የቀረ ተጨማሪ የአንድ አመት ኪራይ ክፍያ ብር 3,450,000.00 (ሶስት ሚሊዮን አራት መቶ አምሳ ሺህ ብር) ተጠሪ እንዲከፍለኝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 208 መሰረት ይታረምልኝ ሲሉ የጠየቁትን ጥያቄ በተመለከተ መልስ ስለሚሻዉ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ/ 208 መሰረት ሊታረሙ የሚገባቸዉ ምን አይነት ስህተቶች ናቸዉ ? የሚሉትን በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 153610 ላይ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የተሰጠባቸዉ ጉዳዩችን ስናይ በፍርድ ወይም በዉሳኔ ወይም በትዕዛዝ ላይ የአፃፃፍ ስህተት፣የቁጥር አፃፃፍ ጉድለት ፣ ባልታወቀና ባልታሰበ የተዘለለ የቃል ስህተት ስለመሆኑ በተመለከተ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 236245 ላይ በፍ/ብ/ስ/ስ/ ሕግ ቁጥር 208 መሰረት የሚታረመዉ ነገር የዉሳኔዉን ይዘት የማይቀይርና መሰረታዊ ያልሆኑ ባለማስተዋል የተፈጠረ የጽህፈት ወይም የቁጥር ጉድለቶች ብቻ ስለመሆናቸዉ አስገደጅ ዉሳኔ የተሰጠበት ሲሆን አሁን በእጃችን ባለዉ ጉዳይ አመልካች በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 208 መሰረት ይታረምልኝ ሲሉ የጠየቁት የአንድ አመት ቀሪ የኪራይ ክፍያ ብር 3,450,000.00 (ሶስት ሚሊዮን አራት መቶ አምሳ ሺህ ብር) እንዲከፈላቸዉ በፍ/ስ/ስ/ስ/ሕ ቁጥር 208 መሰረት የቀድሞ ዉሳኔ ይታረምልኝ ሲሉ ያቀረቡት አቤቱታ ሲታይ በቀድሞ ፍርድ ላይ የአፃፃፍ ስህተት፣የቁጥር አፃፃፍ ጉድለት ፣ ባልታወቀና ባልታሰበ የተዘለለ የቃል ስህተት ሳይሆን አመልካች በጠየቁት ሁኔታ ቀሪ የአንድ አመት ኪራይ ክፍያ ብር 3,450,000.00 (ሶስት ሚሊዮን አራት መቶ አምሳ ሺህ ብር) እንዲከፈል ሲሉ ባቀረቡት አቤቱታ መሰረት የቀድሞዉን ዉሳኔ ማረም ማለት የቀድሞዉን ዉሳኔ ይዘት የሚቀይር እና የፍ/ስ/ስ/ስ/ሕ ቁጥር 208 የተደገገበትን ዓላማ የማያሳካ እና ተቀባይነት የሌለዉ በመሆኑ ከዚህ አኳያ አመልካች በፍ/ብ/ስ/ስ/ስ/ሕ ቁጥር 208 መሰረት ያቀረቡት ጥያቄ ከላይ በተጠቀሰዉን የሰበር አስገዳጅ ዉሳኔ በሚጥስ መልኩ ያቀረቡት አቤቱታ መሆኑን የተገነዘብን ስለሆነ አመልካች በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 208 መሰረት ቀደም ሲል የተሰጠዉ ዉሳኔ ይታረምልኝ ሲሉ የቀረቡትን አቤቱታ ፍርድ ቤቱ አልተቀበለዉም፡፡

መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድአፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

**<u>ማስታወሻ</u>፡** - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 248461

ኅዳር 23 ቀን 2017 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ብርቅነሽ እሱባለዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

**አመልካች** - ሃምሳ አለቃ ሽፈራው ተሰማ ቀርበዋል

**ተጠሪ** - ወ/ሮ ከበቡሽ ከበደ ገረሮ ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ አፈጻጸምን የሚመለከት ነዉ፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጋብቻ በፍርድ ቤት ዉሳኔ መፍረሱን ተከትሎ በተሰጠ ዉሳኔ መሠረት እንዲፈጸም ተጠሪ ባቀረበችዉ የአፈፃፀም ክስ አቅርባ ለዚህ ሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነዉ ቤት በሀራጅ እንዲሸጥ ትዕዛዝ ከተሰጠ በኋላ አመልካች የቅድሚያ መብት ይሰጠኝ በማለት ጠይቀዋል፤ አመልካች ለቀረበዉ አቤቱታ በሰጡት መልስ ለአፈፃፀም ምክንያት የሆነዉ ቤት በሀራጅ ለመሸጥ የሚያዳግት፣ ቤቱ መግቢያ እና መዉጫ የሌለዉ እና በእኔ የግል ንብረት ዉስጥ የተከበበ በመሆኑ በሀራጅ ሊሸጥ ስለማይችል የቤቱን ግምት እኔ ስጥቻት ቤቱን እንዳስቀር ይፈቀድልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የቀረበዉን አቤቱታ ከህጉ ጋር መርምሮ ለአፈፃፀም ምክንያት የሆነዉ ንብረት የግራቀኙ የጋራ ሀብት ስለመሆኑ በመዝገብ ቁጥር 126471 ላይ ዉሳኔ ያረፈበት መሆኑን፣ የጋራ ባለመብት የሆነ ሰዉ ደግሞ በሀራጅ የሚሸጥ ንብረት ላይ የቅድሚያ ግዥ መብት ያለዉ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 443 የተደነገገ በመሆኑ ለተጠሪ የቅድሚያ ግዥ መብት ተፈቅዷል፤ አመልካች ግምት ከፍዬ ንብረት ሳስቀር በማለት የጠየቁትን በተመለከተ በግራቀኝ ስምምነት

መሰረት የሚፈፀም እንጂ በምርጫ የሚፈፀም እና የሀራጅ ዉጤት ከቀረበ በኃላ የሚታይ መሆኑን ጠቅሶ አቤቱታዉን ዉድቅ በማድረግ ብይን ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝተዉ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ግራቀችን በማስቀረብ አከራክሮ የቅድሚያ ግዥ መብትን በተመለከተ ባልና ሚስት በጋብቻ ቆይታቸዉ በጋራ ያፈሩት ሀብት በመሆኑና በንብረቱም እኩል ሲጠቀሙ የቆዩ እንደመሆናቸዉ አንደኛዉ በንብረቱ ላይ የተሻለ መብት እንዳለዉ ተቆጥሮ ንብረቱ ለአንደኛዉ የቅድሚያ ግዥ መብት ሊሰጥ የሚችልብት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በተመሳሳይ ጉዳይ አስገዳጅ ትርጉም የሰጠ ሆኖ ሳለ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይህን አስገዳጅ ትርጉም ወደ ጎን በመተዉ ተጠሪ ልዩ የቅድሚያ መብት አላት በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ አግባብነት የለዉም፤ግራቀኙ ሁለቱም የቅድሚያ ግዥ መብት የላቸዉም በማለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ዉሳኔ በመሻር ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡

ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም ይህንኑ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች ግንቦት 25 ቀን 2015 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የአፈፃፀም ችሎቱ ስልጣን ፍርድ ያረፈበትን ዉሳኔ ማስፈፀም ብቻ ሆኖ ሳለ የስር የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፍርድ ካረፈበት ዉሳኔ ዉጭ የግሌ የሆነዉን ቤቴን እና አትክልቶችን የጋራ ነዉ ከተባለዉ ንብረት ጋር በመቀላቀል ተሸጦ ከተጠሪ ጋር እንድንካፈል ማዘዙ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡ በመዝገብ ቁጥር 100680 በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 11 የሚገኝ አጠቃላይ ስፋቱ 557.99 ካ/ሜትር ላይ ያረፈ ቤት እና አትክልት የግሌ ተብሎ የተወሰነ ሲሆን ይህ ዉሳኔ ያልተሻረ እና ፀንቶ ያለ ሲሆን ከዚህ ቦታ ዉስጥ አሁን የጋራ ነዉ የተባለዉ በ61 ካ/ሜትር ላይ ያረፈ ቤት ብቻ በመሆኑ በጋራ እንድንካፈል ማዘዝ የሚገባዉ በዚህ በ61 ካ/ሜትር ላይ ያረፈዉን ቤት ብቻ ሆኖ እያለ የእኔ የግል ንብረት የሆነዉን 496 ካ/ሜትር ጨምሮ እንድንካፈል መታዘዙ ከተሰጠዉ ዉሳኔ ዉጭ እና ተጠሪ ያለአግባብ እንድትበለፅግ የሚያደርግ በመሆኑ ውሳኔው ሊሻር ገባዋል፡፡ የጋራ ተብሎ የተወሰነዉ ንብረት በእኔ የግል ንብረት ዉስጥ ስለሚገኝ ግምት ለተጠሪ ሰጥቼ ቤቱን እንዳስቀር ያቀረቡክት አቤቱታ የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ካለኝ የቀዳሚነት መብት ጋር አይቶ መብቴን ሊጠብቅልኝ ሲገባ በዝምታ ማለፉ እና  የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህን ስህተት ሳያርም ማለፉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት የሰበር ቅሬታቸዉን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አቤቱታዉ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ በአጥር ግቢ ዉስጥ የተሰሩት ቤቶች ከፊሉ የአመልካች የግል ነዉ መባሉን ተከትሎ ይዞታዉ በፕሮፖርሽን ተሰርቶ ሊካፈሉ ወይም ሊሸጥ የሚችልበት አግባብ ሳይጣራ በጥቅሉ ሊከፋፈሉ አይችሉም የመባሉን አግባብነት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል ተብሏል፡፡ በዚሁም መሠረት ተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ነሐሴ 08 ቀን 2015 ዓ/ም አዘጋጅቶ ባቀረበዉ መልስ ፍርድ ያረፈበት ይዞታ በአይነት መከፈል እንደማይችል የክፍለ ከተማዉ መሬት አስተዳደር አካል ያሳወቀ በመሆኑ የአፈፃፀም ችሎቱ በመዝገብ ቁጥር 126471 ሚያዝያ 14 ቀን 2011ዓ/ም በተሰጠዉ ፍርድ መሰረት በሀራጅ ተሸጦ እንዲከፈል ትዕዛዝ የተሰጠ በመሆኑ አመልካች መደበኛ ችሎቱም ሆነ አፈፃፀም ችሎቱ የሰጠዉን ዉሳኔ መሰረት በማድረግ ይግባኝ ጠይቆ ዉሳኔዉ ባልተሻረበት ሁኔታ እንደ አዲስ በሰበር አቤቱታ ማቅረባቸዉ ከስነስርአት ዉጭ በመሆኑ ዉድቅ ሊሆን ይገባል፡፡ በመዝገብ ቁጥር 126471 ሚያዝያ 14 ቀን 2011ዓ/ም በተሰጠዉ ዉሳኔ ላይ የአመልካች የግል ሀብት ነዉ የተባለዉ 40.02 ካ/ሜትር ላይ

ያረፈ አንድ ክፍል ሳሎን እና አንድ ክፍል መኝታ ቤት ብቻ ሲሆን ከዚህ ዉጭ ያለዉ የጋራ ንብረት መሆኑ ተረጋግጦ ዉሳኔ የተሰጠበት ነው፡፡ አመልካች የጋራ ተብሎ የተወሰነዉ 61 ካ/ሜትር ስፋት ያለዉ ቦታ ላይ የተሰራዉ ቤት ነዉ በማለት የሚያቀረበዉ መከራከርያ አዲስ መከራከርያ በመሆኑ ዉድቅ ሊሆን ይገባል፡፡ አመልካች በስር ፍርድ ቤት የቀደምትነት መብት ጥያቄ አላቀረቡም፡፡ የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የቀደምትነት መብት ሲፈቅድልኝ በዉሳኔዉ ቅር ተሰኝተዉ ይግባኝ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዉ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ በጠየቁት ዳኝነት መሰረት ተጠሪ የቀደምትነት መብት የላቸዉም በማለት ፍርድ የሰጠላቸው በመሆኑ አቤቱታ ለሰበር ችሎቱ ማቅረብ የማይችሉ በመሆኑ ያቀረቡት አቤቱታ ዉድቅ ሆኖ አፈፃፀሙ እንዲቀጥል ፍርድ ይሰጥልን በማለት መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል፣ ይህ ችሎትም በስር ፍርድ ቤቶች በተሰጠ ዉሳኔ ላይ የተፈጸመ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡

እንደመረመረዉም ለዚህ ሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነዉ የግራ ቀኝ የጋራ ንብረት መሆኑ በፍርድ የተረጋገጠዉ ቤት በሃራጅ እንዲሸጥ መታዘዙን ተከትሎ የቀዳሚነት ግዢ መብት እንዲጠበቅላቸዉ ተጠሪ የጠየቁ ሲሆን፣ አመልካችም ቤቱ በሃራጅ ሊሸጥ ስለማይችል የቤቱን ግምት ለተጠሪ ሰጥቼ እንዳስቀር ይፈቀድልኝ በማለት አቤቱታ በማቅረባቸዉ ነዉ፡፡ ፍርድ ቤቱም ግምት ከፍሎ ማስቀረት የሚቻለዉ በስምምነት እንጂ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ አለመሆኑን ጠቅሶ በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ ዉድቅ ያደረገ ሲሆን፣ በአንፃሩ ለተጠሪ የቅድሚያ ግዢ መብት በመፍቀድ ብይን ሰጥቷል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በበኩሉ የቀዳሚነት ግዢ መብት ለተጠሪ ሊጠበቅ አይገባም በማለት ከዚህ አኳያ የስር ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ ሽሮታል፡፡ የግራ ቀኝ የጋራ ሀብት የሆነዉን ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት በዓይነት ማካፈል እንደማይቻል ስለመረጋገጡ የስር ፍርድ ቤት ብይን ግልባጭ ያሳያል፡፡ አመልካች ለዚህ ችሎት ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የስር ፍርድ ቤት አፈፃፀሙን የመራዉ በዉሳኔዉ ላይ ከተመለከተዉ ዉጪ ነዉ የሚል ይዘት ያለዉ ክርክር ያቀርባሉ፡፡ ይሁንና አፈፃፀሙን የያዘዉ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በዉሳኔዉ ላይ ከተመለከተዉ ዉጪ እያስፈጸመ ነዉ የሚል አቤቱታ ለፍርድ ቤቱ ስለመቅረቡ የብይኑ ግልባጭ አያሳይም፡፡ አመልካች የስር ፍርድ ቤት በሰጠዉ ብይን ላይ ቅር ተሰኝተዉ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ይግባኝ የተከራከሩትም የጋራ ነዉ የተባለዉ ንብረት የሚገኘዉ በግል ይዞታቸዉ ላይ በመሆኑ እና ራሱን ችሎ ያለ ባለመሆኑ መዉጫና መግቢያ እንደሌለዉ ጠቅሰዉ በሃራጅ መሸጥ የለበትም፤ እንዲሁም ተጠሪ ያቀረቡት የቀዳሚነት ግዢ መብት ጥያቄም ተቀባይነት እንደሌለዉ በመጥቀስ ስለመሆኑ የከፍተኛዉ ፍርድ ቤት ዉሳኔ ይዘት ያሳያል፡፡ ከዚህ ዉጪ አፈፃፀሙ በዉሳኔዉ ላይ ከተመለከተዉ ዉጪ በግል ንብረቴ ላይ እየቀጠለ ነዉ የሚል ክርክር አመልካች አላነሱም፡፡ በርግጥ አፈፃፀሙ በዉሳኔዉ ላይ ከተመለከዉ ዉጪ የግላቸዉ በሆነዉ ንብረት ላይ የቀጠለ ነዉ የሚሉ ከሆነ አመልካች ይህን አቤቱታቸዉን አፈፃፀሙን ለያዘዉ ፍርድ ቤት ሳያመለክቱ እና ፍርድ ቤቱ አቤቱታቸዉን ካልተቀበለም በይግባኝ እንዲታረም ሳይጠይቁ፣ በስር ፍርድ ቤት ያልተነሳን የክርክር ነጥብ በዚህ ችሎት ደረጃ አንስተዉ ሊከራከሩ የሚችሉበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡

እንደሚታወቀዉ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80 (3/ሀ) ላይ በግልጽ እንደተመለከተዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉን ዉሳኔዎች በማረም ላይ የተገደበ ነዉ፡፡ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለዉ አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን፣ ህግ ያላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉን ህግ የሚጠቅስ፣ ለክርክሩ አግባብነት ያለዉ ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለዉ ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፣ በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ዉድቅ በማድረግ የተወሰነ፣ በፍርድ አፈፃፀም ሂደት ከዋናዉ ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትዕዛዝ የተሰጠበት፣ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተወሰነ፣ የአስተዳደር አካል ወይም ተቋም ከህግ ዉጭ የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ በመቃረን የተወሰነ ሲሆን ነዉ፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በሚል የሰበር አቤቱታ ሲቀርብለት ለአቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ ጉዳይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ ከላይ በዝርዝር ከተመለከቱት ሁኔታዎች ዉስጥ ቢያንስ አንዱን ያሟላ ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 10 ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡

ከዚህ ሁሉ አንፃር ሲታይ የስር ፍርድ ቤቶች በሰጡት ዉሳኔ ላይ የተፈጸመ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለ በመሆኑ ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>**ዉሳኔ**</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 297280 ላይ ሚያዝያ 11 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ በሰበር ሥ/ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1) መሠረት ጸንቷል፡፡
2. ይህ ችሎት ሰኔ 15 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ እግድ ተነስቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ፋ/ዘ**

**ማስታወሻ፡** - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

*የሰ/መ/ቁ 250505*
***ህዳር 30 ቀን 2017ዓ/ም***

ዳኞች፡-ሽመክት አሰፋ

እንዳሻው አዳነ

አለማየሁ ሹናራ

ዋዚሞ ዋሲራ

ዘውዲቱ ታደሰ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ እሌኒ ነጋሽ ኪዳኑ

**ተጠሪ፡-** አቶ ክብሮም ገ/መድህን ወርቅነህ- ጠበቃ መሰለ ገ/ሕይወት

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## <u>ፍርድ</u>

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሐምሌ 07 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 302662 በሚያዚያ 26 ቀን 2015 ዓ.ም የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 137738 በሕዳር 26 ቀን 2015 ዓ.ም የሠጠውን ፍርድ በማፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የቤት ኪራይ ውልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡

አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ይዘት በለሚኩራ ክ/ከተማ ወረዳ 08 የቤት ቁጥር አዲስ የካርታ ቁጥር ጨ-3062/96 የሆነ ቤት ተጠሪ ለሆቴል አገልግሎት እንዲጠቀምበት ከቀን 30/06/2010 ዓ.ም ጀምሮ ለ5 አመት በወር ብር 60,000 በ4ኛውና 5ኛው አመት የኪራዩን ገንዘብ 75,000 ብር በማድረግ የኪራይ ውል ስምምነት እንዳደረጉና ነገር ግን ተጠሪ የውል ግዴታውን ባለመወጣቱ አመልካች ለፌደራል

የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክስ አቅርበው በመ/ቁ 126817 በቀን 14/12/13 ዓ.ም ቤቱን እንዲለቅና ያልከፈለውን ተርን ኦቨር ታክስ እንዲከፍል ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡ በአፈጻጸም ሂደት ላይ እያለ ተጠሪ ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 279740 አቅርበው ፍርድ ቤቱም ተጠሪ ቤቱን ሊለቁ አይገባም በሚል የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር ውሳኔ የሰጠ ቢሆንም ተጠሪ በገዛ በፍቃዱ ታሕሳስ 24 ቀን 2014 ዓ.ም ቤቱን ለቆ ወጥቷል፡፡ ስለሆነም  ከሐምሌ ወር 2013 ዓ.ም እስከ ታሕሳስ ወር 2014 ዓ.ም የቤት ኪራይ ሒሳብ ብር 435,000 እና የተጠቀመበት የታህሳስ ወር የውኃ ፍጆታ ብር 5,643 እና የተርን ኦቨር ታክስ ከሚያዝያ 27/2013 እስከ ታህሳስ 24/2014ዓ.ም 8,700 እንዲሁም ተጠሪ የተከራየውን ቤት ሲለቅ በተረከበበት ሁኔታ ለማስረከብ ቢስማማም በቤቱ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰ በመሆኑ ጉዳቶቹንም ዘርዝው በማቅረብ ለተበላሸው ቤት ወደነበረበት ለመመለስ ብር 303,400 እንዲከፍለኝ እንዲወሰን በሚል ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና በፍሬነገር መልስ የሰጠ ሲሆን ይዘቱም ቀደም ሲል በስር ፍርድ ቤት  በመ/ቁ 126817 ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ ጥቅምት 2 ቀን 2014 ዓ.ም 75,000 ብር፣ ጥቅምት 27/2014 ብር 150,000 በባንክ ገቢ ማድረጉን፣ ከፍርድ በኋላ አመልካች በራሳቸውና በአስረካቢዎች ቸልተኝነት ምክንያት ቤቱን ሳይረከቡ ለቆየበት የመክፈል ግዴታ የለብኝም፣ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰጠውን እግድ ማውጣት ባለመቻሌ ሆቴሉን ዘግቼ ቤቱን ለማስረከብ ነጻ አድርጌ ስጠብቃቸው አስረካቢዎቹ በሌላቸው ስልጣን ቤቱ ጉድለት ስላለው ማስረከብ አንችልም በማለት ርክክቡ እንዳይፈጸም በማድረጋቸው እንጂ በቤቱ ስጠቀም አልነበረም፣ ከፍርድ በኋላም የመክፈል ግዴታ የለብኝም፣ ቲኦቲንም በተመለከተ ያቀረቡት የተዘበራረቀ ነው ሊከፈል አይገባም፣ የቤቱ ጉድለት ያልተረጋገጠና ጎድለዋል የተባሉትንም ዕቃዎች ለመተካት በሚል ያስቀመጡት ዋጋ በባለሙያ ሳይሆን እራሳቸው በግምት ነው ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ተጠሪ በጥቅምት ወር 2014ዓ.ም ለአመልካች በአጠቃላይ ብር 225,000 በሁለት ክፍያ ስለመክፈሉ በደረሰኝ እንደተረጋገጠና ይህም ክፍያ ከሃምሌ1 ቀን 2013 ዓ.ም እስከ መስከረም 30 ቀን 2014 የቤት ኪራይ እንደሆነ ተጠሪ ባቀረባቸው የሰው ምስክሮች ማረጋገጡን አመልካች ይህ ክፍያ እንደተቀበሉ ቢያምኑም የሚያዝያ፣ የግንቦትና ሰኔ 2013ዓ.ም ነው ቢሉም ይህን በማስረጃ አለማረጋገጣቸውን በተጨማሪም ቀደም ሲል በነበራቸው ክርክር እስከ ሰኔ 2013ዓ.ም ድረስ ያለው ክፍያ እንደተከፈለ ውሳኔ የተሰጠበት በመሆኑ ከሃምሌ 1/2013 እስከ መስከረም 30/2014 ዓ.ም የተከፈለ መሆኑን፣ ከጥቅምት 30 እስከ ታህሳስ 2014 ዓ.ም ያለውን በተመለከተ የተጠሪ ምስክሮች ከጥቅምት 1/2014ዓ.ም ጀምሮ የሆቴሉን ስራ አቁሞ ቤቱን ነጻ በማድረግ አመልካች እንድትረከባቸው እንዳረጋገጡና በአንጻሩ የአመልካች ምስክሮች ሆቴሉ እስከ ታህሳስ 2014 ዓ.ም ድረስ የሠራ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ምስክር እንዳላቀረቡና ተጠሪ ቤቱን ለማስረከብ ፍቃደኛ ሆነው ባለበት

አመልካች በቤቱ ላይ ጉድለት አለበት በሚልና ጉድለት እንኳን ካለበት ርክክቡ ከተደረገ በኂላ የመብት ጥያቄ ካለ ማቅረብ ሲችሉ ባለመረከባቸው ተጠሪ ሊከፍል እንደማይገባ፣ የተርንኦቨር ታክስን በተመለከተ ከሃምሌ 1/2013 እስከ መስከረም 30/2014 ዓ.ም ከተከፈለው 225,000 ብር የሚሰበሰብ 20% ተጠሪ ከፍያለው የሚል ክርክር ባለማቅረባቸውና በግልጽ ባለመካዳቸው እንዲከፍሉ ፣የታህሳስ ወር የውሃ ክፍያን በተመለከተ ቤቱን አመልካች ባለመረከባቸው ስለሆነ ተጠሪ ሊከፍል አይገባም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ያቀረቡትን ይግባኝ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መርመሮ ተጠሪን መጥራት ሳየስፈልገው ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

የአመልካች ሐምሌ 07 ቀን 2015 ዓ.ም ተጽፎ የቀረበው የሰበር አቤቱታ በሰበር ችሎት ተመርምሮ በአመልካች እና ተጠሪ መካከል በ30/06/2010 ጀምሮ ባለው ኪራይ ውል መሰረት በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 126817 በ14/12/2013 ዓ.ም የተሰጠውን ውሳኔ አፈጻጸም በ04/04/2014 ዓ.ም እንዲታገድ የተደረገ እና የኪራይ ውሉ እንዲቀጥል በይግባኝ ሰሚው ፍርድ በመ/ቁ 279740 በ10/05/14 ዓ.ም ከተወሰነ በሃላ ተጠሪ በዚሁ መሰረት እንዲፈጻም በጠየቀበት ሁኔታ አመልካች ከሐምሌ 2013 እስከ ታህስስ 2014 ዓ.ም በኪራይ ውሉ መሰረት ያልተከፈለ ኪራይ እንዲከፈላቸው ያቀረቡትን ክስ በቀደመው ውሳኔ አፈጻጸም መሰረት የተከፈው ሳይለይ እንዲሁም አመልካች ቤቱን ለመረከብ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ነው በማለት ውድቅ ያደረገበትን አግባብ በስር ፍርድ ቤት ከተሰጡት ውሳኔዎች፣ ከግራ ቀኙ የኪራይ ውል እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንጻር ለመመርመር የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት በታዘዘው መሰረት ተጠሪ በመጋቢት 27 ቀን 2016 ዓ.ም የተጻፈ መልስ ያቀረበ ሲሆን አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን የሚያጠናክር መጋቢት 25 ቀን 2016 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገቡ ጋር እንዲያያዝ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ፣ ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እና ቅሬታው ለሰበር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ነጥብ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደሚቻለው በአመልካች እና ተጠሪ መካከል ከየካቲት 30 ቀን 2010 ጀምሮ በነበራቸው የኪራይ ውል ምክንያት በነበረ ክርክር የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 126817 ነሐሴ 14 ቀን 2013 ዓ.ም የኪራይ ውሉ ፈርሳል፣ ተጠሪ የሚከፍሉት የኪራይ ገንዘብ የለም፣ ያልከፈለውን ተርን ኦቨር ታክስ እንዲከፍል እና ተጠሪ ቤቱን ለቀው እንዲያስረክቡ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ መሰረት እንዲፈጸምላቸው በመ/ቁ 133990 የአፈጻጸም አቤቱታ ያቀረቡ እና ፍርድ ቤቱም ህዳር 30 ቀን 2014 ዓ.ም በፍርዱ መሰረት እንዲፈጸም ያዘዘ ቢሆንም ተጠሪ በዋናው ጉዳይ ይግባኞቻቸውን ነሐሴ 25 ቀን 2013 ዓ.ም በመ/ቁ 279740 ለፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው የነበረ

በመሆኑ አፈጻጸሙ እንዲታገድላቸው ታህሳስ 1 ቀን 2014 ዓ.ም ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት በዚያው ዕለት የስር ፍርድ ቤት አፈጻጸም እንዲታገድ ታዟል፡፡

ይህ በእንዲህ እያለ ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነው አመልካች ከፍርዱ በሃላ አመልካች ከሐምሌ 2013 እስከ ተጠሪ በፈቃዳቸው ለቀው አስከወጡበት ታህስስ 2014 ዓ.ም ድረስ ያለውን ኪራይ፣ የውሃ፣ተርን ኦቨር ታክስ እና ቤቱን ለቀው በነበረበት ሁኔታ ያስረክቡኝ በማለት መጠይቀው የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ በክርክር ወቅት የከፈሉት በዚሁ ግዜ እንደተከፈለ በመውሰድ እንዲሁም ተጠሪ ከጥቅምት 1 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ አቁሞ ቤቱን ለማስረከብ ዝግጁ የነበረ ቢሆንም ቤቱ ጉድለት አለበት በሚል ፈቃደኛ ያለሆኑ በመሆኑ ተጠሪ ሊከፍል አይገባም በማለት ሌሎች ክፍያዎችን መወሰኑን የሚመለከት ነው፡፡ ስለሆነም ምላሽ የሚፈልገው ነጥብ አመልካች ከሐምሌ 1 ቀን 2013 እስከ ታህስስ 2014 ዓ.ም ድረስ ያለውን ኪራይ ተጠሪ የመክፈል ሃላፊነት ያለባቸው መሆን አለመሆኑን እና መጠኑን፣ አመልካች ክፍያ የጠየቁበትን ተርን ኦቨር ታክስ፣የውሃ ክፍያ እና በመጨረሻም በነበረበት ሁኔታ ማስረከብን የሚመለከቱት ጭብጦች ናቸው፡፡

በመሰረታዊነት በግራ ቀኛቸዉ መካከል የተደረገዉ የማይንቀሳቀስ ንብረት ኪራይ እንደመሆኑ መጠን ይህን የኪራይ ዉል መነሻ በማድረግ ለሚነሳዉ ክርክር በቀዳሚት ተፈጻሚነት ያለዉ የፍ/ሕ/ቁ.2896 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሆናቸዉን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ በፍ/ሕ/ቁ 2900 መሰረት አከራይ ያከራየዉን የማይንቀሳቀስ ንብረት በዉሉ መሰረት ለተከራይ የማስረከብ ግዴታ እንዳለበት ሁሉ ተከራይ ይህን በዉል የተከራየዉን የማይንቀሳቀስ ንብረት በዉሉ አግባብ ለተጠቀሰዉ ዓላማና በሕግ በተመለከተዉ አግባብ የመገልገል ግዴታ ያለበት እና የኪራዩ የዉል ጊዜ ሲያልቅ የማንቀሳቀሰዉን ንብረት እና ከዚህ ንብረት ጋር የተቀበላቸዉን ነገሮች ለአከራዩ የመመለስ ግዴታ ያለበት መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁ.2936 ድንጋጌ ሥር ተደንግጓል፡፡ የማንቀሳቀስ ንብረት የኪራይ ዉል ደግሞ በአመልካችና ተጠሪ መካከል ሕግ መሆኑን ከፍ/ብ/ሕ/ቁ.1677 (1) እና 1731 ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ ስለሆነም ተዋዋይ ወገኖች በኪራይ ውሉ መሰረት እንዲፈጽሙ ይገደዳሉ፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ከአመልካች በተከራየው ቤት አስከ ታህሳስ 2014 ዓ.ም አንደቆየ በግራ ቀኙ የተካደ ካለመሆኑም በላይ በስር ፍርድ ቤትም በክርክሩ ወቅት በጥቅምት ወር በአጠቃላይ ብር 225,000 የከፈለ ስለመሆኑ በተጨማሪ የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች ናቸው፡፡ ስለሆነም ቀሪውን ከጥቅምት እስከ ታህሳስ ያለውን በተመለከተ ተጠሪ ቤቱን ለማስረከብ ፈቃደኛ ሆነው ዝግጁ ቢሆኑም አመልካች ቤቱ ጉድለት አለበት በማለት ባለመረከባቸው የቆዩበት በመሆኑ ተጠሪ ሊከፍሉ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡

ከስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ይዘት መረዳት የሚቻለው ክርክሩን ለማስረዳት የቀረበው የሠው ማስረጃ መሠረት አድርጎ ውሳኔ የሰጠ ስለመሆኑ ነው፡፡ በሌላ በኩል ግራቀኙ በዚህ ፍርድ ቤት ባደረጉት ክርክር ሆነ የስር ፍርድ ቤት እና ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትን መዝገብ እንደተመለከት ነው ተጠሪ ቤቱን ለቀው

እንዲያስረክቡ ተወሰነ ቢሆንም በበቤቱ ውስጥ ሁነው ክርክር ላይ የነበሩ መሆኑን ነው፡፡ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 182(1) እንደተመለከተው በመጀመሪያ ደረጃ የሚሰጥ ፍርድ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን መነሻ ጉዳይ በአጭሩ የሚገልጽ መሆን አለበት የሚለው የቀረበውንም ማስረጃ ይዘት የሚመለከት ነው፡፡ ፍርድ በሚሰጥበት ጊዜም ምክንያትን ማስፈር እንደሚገባ በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ አንቀጽ 182(1) የተመለከተ ግዴታ ነው፡፡ ፍርድ በሚጻፍበት ጊዜ ስለጉዳዩ መግቢያ፣ በክርክሩ የተነሱትን ፍሬ ነገሮች ማስፈር፣ ምላሽ የሚያስፈልገውን የፍሬ ነገር ወይም የሕግ ጭብጥ መለየት፣ በተለየው ጭብጥ ማስረጃውን በመመዘን እና ተፈጻሚነት ያለውን ሕግ በመተግበር እና/ወይም በመተርጎም ለውሳኔው ምክንያትን በማስፈር ተፈጻሚ የሚሆነውን ዳኝነት የተጠቀበትን ጉዳይ እልባት መሥጠትን ይጠይቃል፡፡ በዚህም ተከራካሪ ወገን በአግባቡ የተሰማ፣ ማስረጃው በአግባቡ ግምት ውስጥ የገባና ዳኛው ሕጉን እና የቀረበውን ማስረጃ መሠረት አድርጎ የወሰነው ስለመሆኑ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ በፍትሐ ብሔር ክርክር የምንከተለው የማስረዳት ደረጃ ከሁለቱ ወገን የተሻለ ያስረዳው ማን ነው (preponderance of evidence) የሚለውን በመመርመር ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የቀረበውን ማስረጃ በመሉ አለመመዘኑ ያሰገነዝባል፡፡

በስር ፍርድ ቤት ከተረጋገጡትና ከላይ ከተገለጹት ፍሬ ነገሮች መገንዘብ እንደሚቻለው ተጠሪ ቤቱን ለቀው እንዲስረክቡ ውሳኔ ከተሰጠ ነሐሴ 14 ቀን 2013 ዓ.ም በሃላ በመ/ቁ ይግባኛቸውን ወድያውኑ ነሐሴ 25 ቀን 2013 ዓ.ም በመ/ቁ 279740 ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረባቸው እና ክፍያ ፈጸምኩ ካሉበት ጥቅምት በሃላ አፈጻጸሙ እንዲታገድላቸው ታህሳስ 1 ቀን 2014 ዓ.ም ለፍርድ ቤቱ አቤቱታ አቅርበው የዕግድ አቤቱታ እንዲሰት መሆኑ አመልካች ባለመረከባቸው ምክንየት ነው በቤቱ የቀየሁት በማለት የሚያቀርቡት መከራከሪያ በስር ፍርድ ቤቶች ከተረጋጋጠው አንጻር ተቀባይነት ያለው ሁኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ አመልካች እስከ ታህሳስ 30 ቀን 2014 ዓ.ም ያልተከፈለ ኪራይ ሂሳብ ብር 435,000 ውስጥ በስር ፍርድ ቤት በክርክር ወቅት ተጠሪ መክፈላቸው የተረጋገጠው ብር 225,00 ሲሆን ቀሪ ክፍያውን ብር 210,000 አመልካች ለተጠሪ ሊከፍሉ የሚገባ ሁኖ ተገኝቷል፡፡

በአጠቃላይ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሐምሌ 1 ቀን 2013 እስከ ታህሳስ 30 ቀን 2014 ዓ.ም ያለውን ቤት ኪራይ ክፍያ ሊከፍል ኤገባም በማለት የሰጠው እና በይግባን ሰሚው ፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የጸናው ውሳኔ የግራቀኙን ማስረጃ በተገቢው ሁኔታ የማስረጃ ተቀባይነትና ለማስረጃው የሚሰጠውን ክብደት (weight of evidence) በመለየት እንዳልወሰነ የሚያስገነዝብ እና የተከራካሪዎች በእኩልነት የመደመጥ መብት ያለመከበሩን የሚያረጋግጥ ስለሆነ ሊታረም የሚገባው መሠረታዊ የሆነ የማስረጃ ምዘና መርሕ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ውሳኔ**

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 302662 በሚያዚያ 26 ቀን 2015 ዓ.ም የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 137738 በሕዳር 26 ቀን 2015 ዓ.ም የሠጠውን ፍርድ በማፅናቱ የሰጠው ትእዛዝ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1//ሀ/መሰረት  መሰረት ተሽሽሏል፡፡
2. ተጠሪ ከሐምሌ 1 እስከ ታህሳስ 30 ቀን 2014 ዓ.ም ያለው ኪራይ ሊፍል አይገባም በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽራል፡፡
3. ከሐምሌ 1 ቀን 2013 እስከ ታህሳስ 30 ቀን 2014 ዓ.ም ያለው ቀሪ ክፍያ ኪራይ ብር 210,000(ሁለትመቶ አስር ሺ ብር) ተጠሪ ለአመልካች ሊከፍል ይገባል፡፡
4. ሌሎች የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው እና በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የጸናው ውሳኔ አልተለወጠም፡፡
5. አመልካችና ተጠሪ በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል**፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

**ማስታወሻ**፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
## የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መዝገብ ቁጥር - 250606

ቀን - 30/03/2017 ዓ/ም

ዳኞች - ሽመክት አሰፋ

እንዳሻው አዳነ

አለማየሁ ሹናራ

ዋዜሞ ዋሲራ

ዘውዲቱ ታደሰ

አመልካች - አቶ ዳምጤ አድማሱ - የቀረበ የለም

ተጠሪ - ወ/ሮ ሀረገወይን ብርሃነመስቀል - የቀረበ የለም

መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው ለምርመራ ስለሆነ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ አመልካች 2ኛ ተከሳሽ ተጠሪ ከሳሽ ሲሆኑ አሁን የክርክሩ አካል ያልሆነው አቶ ሽመልስ መንገሻ 1ኛተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የስር ከሳሽ የአሁን ተጠሪ በስር ተከሳሾች ላይ ያቀረቡት ክስ ይዘት ከሳሽ ባልሰጠሁት ውክልና ውክልና እንደሰጠሁት በማድረግ በሀሰተኛ ውክልና ከ 2ኛ ተከሳሽ ጋር የቤት ሽያጭ ውል ፈፅመዋል፡፡ የተሸጠው ቤት የከሳሽና 1ኛ ተከሳሽ የጋራ ንብረት ነው፡፡ የከሳሽና 1ኛ ተከሳሽ ጋብቻ በፍርድ ቤት ፈርሷል፡፡ የተሸጠው ቤት የከሳሽና 1ኛ ተከሳሽ የጋራ ቤት በመሆኑ ያለ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

እኔ ስምምነት የተፈፀመ የሽያጭ ውል በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 68 መሰረት የቤት ሽያጭ ውል እንዲፈርስ የሚል ነው፡፡የስር 1ኛ ተከሳሽ መጥሪያ በቤቱ ላይ ቢለጠፍም መልስ ባለማቅረቡ መብቱ ታልፏል፡፡ ከ 2ኛ ተከሳሽ የአሁኑ አመልካች የተሰጠው በአጭሩ የቤት ሽያጭ ውል በህጋዊ መንገድ በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ፅ/ቤት ቀርቦ ተመዝግቧል፡፡ ቤቱን የገዛሁት ከከሳሽና ከ 1ኛ ተከሳሽ ወኪል ላይ ገዝቻለሁ የከሳሽና 1ኛ ተከሳሽ ወኪል የሆኑት ወ/ሮ ታሪኳ ገዛኸኝ በውል አዋዋይ ፊት የገዛሁት ስለሆነ ውሉ ሊፈርስ አይገባም 2ኛ ተከሳሽ የቅን ልቦና ገዥ ስለሆንኩ ውሉ ሊፈርስ አይገባም፡፡ ቤቱን ከተረከብኩ በኃላ በቤቱ ላይ ብር 600,000 በላይ አውጥቼ ግንባታ ፈፅሚያለሁ ለቤት ግዥ ካወጣሁት ከብር 3,200,000 ጋር በአጠቃላይ 3,800,000 ብር ወጪ አውጥቻለሁ ውሉ ሊሰረዝ አይገባም ተብሎ እንዲወሰን በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ የፅሁፍ እና የቃል ክርክር ከተጠናቀቀ በኃላ ፍርድ ቤቱ የቤት ሽያጭ ውል ያለሚስትና ባል ፍቃድ ውጪ የተፈፀመ ነው ወይስ አይደለም? ውሉ ሊፈርስ ይገባል ወይስ አይገባም? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ መዝገቡን መርምሮ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት የከሳሽና 1ኛ ተከሳሽ ባልና ሚስት የጋራ ንብረት መሆኑን በከሳሽና 1ኛ ተከሳሽ መካከል ያለው ጋብቻ በፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 104009 የፈረሰ መሆኑን አከራካሪው ቤት የተሸጠው በከሳሽና 1ኛ ተከሳሽ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍርድ ቤት እንዲፈርስ ከተወሰነ በኃላ የንብረት ክፍፍል ከመደረጉ በፊት መሆኑን የባልና የሚስት የማይንቀሳቀስ የጋራ ንብረት ለ 3ኛ ወገን ለማስተላለፍ የሁለቱ ተጋቢዎች ስምምነት የሚያስፈልግ ስለመሆኑ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 68(1)(ሀ) ስር በግልፅ ተደንግጎ የሚገኝ መሆኑን የጋራ ስምምነት ሳይኖር አንደኛው ተጋቢ ከሌላ 3ኛ ወገን ጋር ውል ገብቶ ከሆነ ሌላኛው ተጋቢ ግዴታ መግባቱን ባወቀበት በ 6 (ስድስት) ወር ውስጥ ክስ ማቅረብ እንደሚችሉ የሚደነግግ መሆኑን የከሳሽ ዳኝነት ጥያቄ የሽያጭ ውሉ የተደረገው በባልና ሚስት የጋራ ንብረት ላይ ያለ ሚስት ፍቃድ በሀሰተኛ ውክልና በመሆኑ ውሉ ሊፈርስ ይገባል የሚል መሆኑን፣ 1ኛ ተከሳሽ ሀሰተኛ መታወቂያ እና ሀሰተኛ የጋብቻ ምስክር ወረቀት ያወጣ መሆኑን ለ 1ኛ ተከሳሽ እህት ከሳሽ ሰጠች የተባለው ውክልና ከሳሽ ያልሰጠች መሆኑን ተሰጠ የተባለው ውክልና የከሳሽ እንዳልሆነ ከሚመለከታቸው አካላት የተረጋገጠ መሆኑን 1ኛ ተከሳሽ የባልና ሚስት የጋራ ሀብት የሆነውን ቤት ከፍቺ በኃላ ሀሰተኛ መታወቂያና ሀሰተኛ የጋብቻ ምስክር ወረቀት በማውጣት ለእህቱ ከሳሽ ውክልና እንደሰጠች በማስመሰል ሀሰተኛ ሰነድ በማቅረብ አጭበርብረው ከሳሽ ውክልና ባልሰጡበት ሁኔታ የከሳሽ ውክልና ለእህቱ ለወ/ሮ ታሪኳ ገዛኸኝ እንዲሰጥ በማድረግ የጋራ ሀብቱን ለ 2ኛ ተከሳሽ እንዲሸጥ ያደረገ መሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ መሆኑን፣ 2ኛ ተከሳሽም ውክልናው የተጭበረበረ መሆኑንና ማስረጃዎቹም ሀሰተኛ መሆናቸውን

የሚያውቅ መሆኑን ከሳሽ ያላስረዱ መሆናቸውን የሽያጭ ውል በህጋዊ አካላት ፊት ቀርቦ የተፈፀመ በመሆኑ 2ኛ ተከሳሽ የቅን ልቦና ገዥ መሆኑን 1ኛ ተከሳሽ በቤቱ ላይ ግማሽ ድርሻ ያለው መሆኑን ግማሽ ድርሻውን ትዳሩ የፈረሰ ስለሆነ ለፈለገው ሰው ማስተላለፍ የሚችል መሆኑን በድርሻው ላይ ያደረገው ውል አግባብ መሆኑን የቤት ሽያጭ ውሉ የተፈፀመው በከሳሽና 1ኛ ተከሳሽ በሆነው በጋራ ንብረት ላይ በመሆኑ በከሳሽ ድርሻ ላይ የሽያጭ ውል ውጤት የሌለው በመሆኑ በከሳሽ ድርሻ ላይ የተፈፀመ የሽያጭ ውል ሊፈርስ ይገባል፡፡ 1ኛ ተከሳሽ ከተቀበለው ገንዘብ ውስጥ ብር 1,600,000 ከህጋዊ ወለድ ጋር ለ 2ኛ ተከሳሽ እንዲመልስ 2ኛ ተከሳሽ 1ኛ ተከሳሽን በመተካት ቤትና ይዞታ ከከሳሽ ጋር እኩል ድርሻ ያላቸው በመሆኑ የጋራ ባለሀብቶች ናቸው በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡

የአሁን ሰበር ቅሬታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች ቅር በመሰኘት ሲሆን የሰበር ቅሬታውም በአጭሩ ተጠሪ ለተወካይ ወ/ሮ ታሪኳ ገዛኸኝ የሰጡት ውክልና ስልጣን ባለው አካል ቀርቦ የተመዘገበ መሆኑን ተጠሪ እና በስር ፍርድ ቤት 1ኛ ተከሳሽ ተወካይ ወ/ሮ ታሪኳ ገዛኸኝ በህጋዊ መንገድ በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ፅ/ቤት ቀርቤ የፈፀምኩት የሽያጭ ውል በከፊል እንዲፈርስ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ በወኪላቸው አማካኝነት የሸጡት የሽያጭ ውል በከፊል እንዲፈርስ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ተሽሮ የቤት ሽያጭ ውሉ በከፊል ሊፈርስ አይገባም ተብሎ እንዲወሰን የሚል ነው፡፡

ይህ ችሎት በአመልካችና በስር 1ኛ ተከሳሽ አቶ ሽመልስ መንገሻና በተጠሪ ተወካይ ወ/ሮ ታሪኳ ገዛኸኝ መካከል በ 25/09/2013 ዓ.ም የተደረገው የሊዝ መብት ሽያጭ ውል አመልካች በሰነዶች ማረጋገጫ ተሰጠ የተባለው ውክልና የቀረበው የጋብቻ ማስረጃ ሀሰተኛ መሆናቸውን ያውቅ የነበረ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም በማለት የቅን ልቦና ገዥ ነው ካለ በኃላ የሽያጭ ውሉ በከፊል ሊፈርስ ይገባል ሲል የሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 28(3) እና ይህንኑ ለማስፈፀም በወጣው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስነ ስርአት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 7(2) መሰረት ተጠሪ ቀርበው መልስ እንዲሰጡ በመታዘዙ ምክንያት ተጠሪ የበኩላቸውን መልስ በ 04 ገፅ አቅርበው ከመዝገቡ ጋር የተያያዘ ሲሆን ፍሬ ቃሉ በአጭሩ ክርክር የተነሳበት የማይንቀሳቀስ ሀብት የተጠሪና የስር 1ኛ ተከሳሽ የጋራ ንብረት መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ በተጠሪ እና በስር 1ኛ ተከሳሽ መካከል የነበረው ጋብቻ ከፈረሰ በኃላ ጋብቻ እንዳለ በማስመሰል በሀሰተኛ ጋብቻ ምስክር ወረቀትና በሀሰተኛ ውክልና የቤት ሽያጭ ውል መፈፀሙ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ቤቱን ከመግዛቱ በፊት ተጠሪ እና

1ኛ ተከሳሽ በንብረቱ ላይ ክርክር ላይ መሆናቸውን ከሚመለከተው ክፍል ማስረጃ ቀርቦ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ቅን ልቦና ገዥ አይደለም፡፡ አመልካች ቤቱን የገዛው ተጠሪ እና የስር 1ኛ ተከሳሽ አከራካሪ ቤቱን በተመለከተ በክርክር ላይ መሆናችንን ስለሚያውቅ የቅን ልቦና ገዥ አይደለም፡፡ በህገወጥ ማስረጃ ከቅን ልቦና ውጪ የተፈፀመ የሽያጭ ውል ሙሉ በሙሉ እንዲፈርስ ሲል በሰበር መዝገብ ቁጥር 51034፣ 60720 እና 45370 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠበት በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት የሽያጭ ውሉ ሙሉ ለሙሉ እንዲፈርስ መወሰን ሲገባ ውሉ በከፊል እንዲፈርስ በከፊል ሊፀና ይገባል ማለቱ ስህተት ነው የሚል ነው፡፡ አመልካች የመልስ መልሱን በ 13/09/2016 ኢ.ም በ 02 ገፅ ሰበር ቅሬታውን በማጠናከር አቅርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ በተገለፀው መሰረት የተጠቃለለ በመሆኑ እኛም ለሰበር ቅሬታ መነሻ የሆነውን ፍርድ የግራ ቀኙን ክርክር ከማስቀረቢያ ነጥብ አንፃር የቤት ሽያጭ ውሉ በከፊል እንዲፈርስ የተወሰነው በአግባቡ መሆን አለመሆኑን በጭብጥነት በመያዝ አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

መርምረን እንደተረዳነው ከሆነ የአሁን ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ከስር 1ኛ ተከሳሽ ጋር ባልና ሚስት መሆናቸውን ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት የጋራ ቤታቸው መሆኑን በመካከላቸው የነበረው ጋብቻ የፈረሰ ቢሆንም የንብረት ክፍፍል ያልተደረገ መሆኑን የ 1ኛ ተከሳሽ እህት ታሪኳ ገዛኸኝ ከሳሽ ያልሰጡትን ሀሰተኛ ውክልና በመያዝ የጋራ ንብረት የሆነውን ቤት ያለ እኔ እውቅና ለ 2ኛ ተከሳሽ የሸጠቸው የሽያጭ ውሉ በሀሰተኛ የጋብቻ ምስክር ወረቀት እና በሀሰተኛ ውክልና የተፈፀመ ውል ስለሆነ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 68(1)(ሀ) መሰረት እንዲፈርስልኝ የሚል ነው፡፡ አመልካች በስር ፍርድ ቤት በሰጠው መልስ የወ/ሮ ታሪኳ ገዛኸኝ ውክልና በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ፅ/ቤት ቀርቦ የፀደቀ ውክልና መሆኑን የቤት ሽያጭ ውል በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ፅ/ቤት ቀርቦ የፀደቀ መሆኑ ውክልና የከሳሽ ያለመሆኑን የማያውቅ መሆኑን የቅን ልቦና ገዥ መሆኑን ቤቱን ከገዛ በኃላ ብዙ ወጪ በማውጣት ተጨማሪ ግንባታ የገነባ በመሆኑ የሽያጭ ውሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡

አመልካች ቤቱን የገዛው ከወ/ሮ ታሪኳ ገዛኸኝ እጅ ነው፡፡ ወ/ሮ ታሪኳ ገዛኸኝ ቤቱን በምትሸጥበት ጊዜ የተጠሪና የስር 1ኛ ተከሳሽ ውክልናን በመያዝ ነው፡፡ ወ/ሮ ታሪኳ ገዛኸኝ ቤቱን ለመሸጥ የሚያስችላት ውክልና ከተጠሪ እና ከስር 1ኛ ተከሳሽ ይዛለች አመልካችም ውክልናው በህጋዊ አካላት ፊት ቀርቦ የፀደቀ መሆኑን በማየት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ወ/ሮ ታሪኳ የያዘችውን ውክልና ተጠሪ ያልሰጡትና ሀሰተኛ ውክልና መሆኑን ማስረጃ የመመርመርና የመመዘን ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ ውክልናው ሀሰተኛ እና ተጠሪ ያልሰጡት ውክልና በመሆኑ ለክርክሩ

ማሳ ታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

መነሻ የሆነውን ቤት አመልካች የገዛው ከተጠሪ ፍላጎትና ስምምነት ውጪ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ የባልና የሚስት የጋራ ንብረት የሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት ለሌላ 3ኛ ወገን ለማስተላለፍ የሁለቱ የጋራ ስምምነት እንደሚያስፈልግ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 68(1)(ሀ) ስር በግልፅ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ አንፃር የሽያጭ ውሉ ህጋዊ አሰራርን የተከተለ አይደለም፡፡ በስር ፍርድ ቤት አመልካች የቅን ልቦና ገዥ ያለመሆኑን ተጠሪ አላስረዱም ማለቱ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የቅን ልቦና ግዥ መሆኑን የማስረዳት ግዴታ ያለበት አመልካች ነው እንጂ ተጠሪ አይደለም፡፡ ከዚህ አንፃር አመልካች የቅን ልቦና ገዥ መሆኑ በስር ፍርድ ቤት አልተረጋገጠም፡፡ የስር ከሳሽና 1ኛው ተከሳሽ ቀበሌ እና የአመልካች ቀበሌ አንድ ከመሆኑ አንፃር ተጠሪ እና ስር 1ኛ ተከሳሽ ባልና ሚስት መሆናቸው ጋብቻቸው በፍርድ ቤት ፈርሶ የንብረት ክርክር ላይ መኖራቸውን አመልካች ያለማወቁን ማስረዳት ይጠበቅበታል፡፡ ይሁን እንጂ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ቅን ልቦና ገዥ ነው በማለት በሰጠው ውሳኔ ላይ ተጠሪ ስላልመጡ አመልካች የቅን ልቦና ገዥ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ የዚህ ችሎት ጭብጥ ሊሆን ስለማይችል አልፈን አመልካች የቅን ልቦና ገዥ ስለሆነ ውሉ ሙሉ በሙሉ ሊፈርስ አይገባም በከፊል የተጠሪ ድርሻ ላይ የተፈፀመው የሽያጭ ውል ሊፈርስ ይገባል በማለት የሰጠው ፍርድ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

ሲጠቃለል ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት የስር 1ኛ ተከሳሽ እና የተጠሪ የጋራ ንብረት መሆኑ በስር 1ኛ ተከሳሽ እና ተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍርድ ቤት መፍረሱ የጋራ ንብረት ክፍፍል ያልተደረገ መሆኑ ቤቱን ለአመልካች በሽያጭ ያስተላለፉት ወ/ሮ ታሪኳ ገዛኸኝ ከተጠሪ ውክልና ሳይሰጣት በሀሰተኛ ውክልና የሸጠች መሆኑ ማስረጃ የመመዘንና የመመርመር ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ተረጋግጦ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት አላገኘንም፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 146459 በቀን 17/05/2015 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 302739 በቀን 19/08/2015 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት ባለመኖሩ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስነ ስርአት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9(1)(ሀ) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻቻሉ፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

4. በዚህ መዝገብ የተሰጠ እግድ ካለ ተነስቷል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 250756

ህዳር 26 ቀን 2017 ዓ.ም

**ዳኞች**፡-ሽመክት አሰፋ

አለማየሁ ሹናራ

ተናኜ ጥላሁን

ዋዚሞ ዋሲራ

ዘውዲቱ ታደሰ

አመልካች፡- ሀበሻ ሲሚንቶ አክሲዮን ማህበር አልቀረቡም

ተጠሪ፡- አያት አክሲዮን ማህበር አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

**ፍርድ**

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሐምሌ 11 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ ችሎት በመ/ቁ 03219 በቀን 10/09/2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 306130 በቀን 30/10/2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ስለጠየቁ ነው።ጉዳዩ ውል የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁን ተጠሪ በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአሁን አመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ነው። የአሁን ተጠሪ ግንቦት 10 ቀን 2015 ዓ.ም በተጻፈ ባቀረበው ክስ አመልካች ከተጠሪ ድርጅት አጠቃላይ 10,800 (አስር ሺህ ሰምንት መቶ) ኩንታል ሲሚንቶ ለመግዛት በመስማማት አመልካች ክፍያ ለተጠሪ ፈጽመናል። ተጠሪ በተለያየ ጊዜ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

4398 ኩንታል ያቀረበልን ሲሆን ቀሪውን 6402 ኩንታል ሲሚንቶ እንዲያቀርቡልን በተደጋጋሚ የጠየቅን ቢሆንም ተከሣሽ ሲምንቶውን ለማቅረብ ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ ስለሆነም አመልካች ክፍያ ተፈጽሞለት ማስረከብ የነበረበትንና ያላቀረበውን 6,402 ኩንታል ሲሚንቶ ለተጠሪ እንዲያስረክብ እንዲሁም ተጠሪ በዚህ ክስ ምክንያት ያወጣነውን የዳኝነትና ሌሎች ወጪዎችን ኪሳራ ጭምር እንዲከፍለን ይወሰንልን በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

ተከሳሽ ወይም የአሁን አመልካች ባቀረበው መልስ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ውል ስለመኖሩ እንዲሁም፣ በክሳቸው መሰረት ክፍያ ስለመፈፀማቸው እንዲሁም  በውል መሰረት ከአመልካች 4398 ኩንታል ሲሚንቶ የተረከቡ መሆኑን የሚያስረዳ ማረጃ አላቀረቡም:: ክፍያ ተፈፅሟል እንዲሁም አመልካች 6,402 ኩንታል ሲሚንቶ ይቀርበታል ቢባል እንኳን አመልካች ሳይፈፅም የቀረው ባጋጠሙት ከአቅም በላይ በሆኑ ችግሮች ማለትም በመንግስት የከሰል ድንጋይ ኢምፖርት እንዳይደረግ ትዕዛዝ በመተላለፉ፣  ጋምቤላ አካባቢ የድንጋይ ከሰሉ ባለበት አከባቢ የፀጥታ ችግር በመከሰቱና የድንጋይ ከሰል ማመላለስ ባለመቻሉ፣ የአመልካች ሰራተኞች ታፍነው በመወሰዳቸው፣ መንገድ በመዘጋቱ የአመልከች ፋብሪካ ለወራት ስራ እንዲያቆም ያደረገው ከመሆኑ በተጨማሪ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር በሐምሌ 04 ቀን 2014 ም 0/1/811/33730 የሲሚንቶ  ግብይት እና ስርጭትን በሚመለከት ያወጣውን መመሪያ ሲሚንቶ ፋብሪካዎች ለተደለደሉበት ቦታዎች ብቻ ሲሚንቶ እንዲያከፋፍሉ ግዴታ መጣሉ፤ መመሪያ ፋብሪካዎች የምርታቸውን 20 በመቶ ብቻ እንዲያስረክቡ በመታዘዙ ሽያጭ የፈጸምንባቸውን እና ገንዘብ የተቀበልንባቸውን ምርቶች በአንድ ጊዜ ለማስረከብ ተቸግረናል፡፡፡

አመልካች ከአቅም በላይ የሆነበት ችግር ተቀርፎለት ማምረት ሲጀምር ምርት ለከሳሽ ይስጥ ቢባል እንኳን አሁን ላይ 1 ኩንታል ለሚንቶ ከ 1,200 ብር በላይ በመሆኑ በፍ/ብሔር ሕጉ አንቀጽ 1793 (ሀ) እና (ለ) ተጠሪ ልዩነቱን ከፍለው ሊረከቡ ይገባል እንጂ ከዚህ ቀደም በከፈሉት ሂሳብ አሁን ላይ 6,402 ኩንታል ሲሚንቶ ሊሰጣቸው አይገባም። ስለሆነም አመልካች የሚያስረክበው ምርት ስለሌለው ተጠሪ የከፈሉት የ6,402 ኩንታል ሲሚንቶ ገንዘብ ካለ ተመላሽ እንዲደረግላቸው እንዲወሰን። ይህ ባይሆን ግን ከሣሽ የከፈሉትን እና አሁን ያለውን የዋጋ ልዩነት ታሳቢ በማድረግ 1 ኩንታል ሲሚንቶ በ 1,200ብር ሂሳብ ልዩነቱን ከፍለው ይረከቡ ተብሎ እንዲወሰን፤ እንዲሁም በመመሪያው መሠረት የምርታችንን 20 በመቶ ብቻ ለማስረከብ ስለምንገደድ እና ያለብን የደንበኞች ውዝፍ ሲሚንቶም ከፍተኛ በመሆኑ ይሄው ታሳቢ ተደርጎ ርክክብ እንድናደርግ እንዲወሰን እና ክሱ ያስከተለውን ኪሰራ ተጠሪ እንዲተኩ ተደርጎ በነፃ እንድንሰናበት ይወሰንልን በማለት አቅርበዋል፡፡

ፍሬ ጉዳዩን በማስረጃ የማጣራትና የመመዘን ስልጣን ያለው የስር ፍ/ቤት የግራቀኙን የጽሁፍና የቃል ክርክር ከሰማና በማስረጃ ካጣራ  በኋላ አመልካች ክስ የቀረበበትን ሲሚንቶ ለተጠሪ ሊያስረክብ ይገባል ወይስ አይገባም? የሚለውን ጭብጥ በዋነኝነት በመያዝ ለዚህ በዋናነት ለተያዘው ጭብጥ ምላሽ ለመስጠት በቅድሚያ በግራቀኙ መካከል

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

የተደረገ የሲሚንቶ ሽያጭ ውል ስምምነት መኖር አለመኖሩን? ውል አለ ከተባለ ተከሣሽ በውሉ መሠረት ሲሚንቶ ለማስረከብ ሊገደድ የሚገባ መሆን አለመሆኑን የተመለከተ ሲሆን በቀዳሚነት የተያዘውን ነጥብ በተመለከተ ከሣሽ ከተከሣሽ ጋር የሲሚንቶ ሽያጭ ስምምነት ያደረገ መሆኑን ለማስረዳት በማስረጃነት ያቀረቧቸውን ሠነዶች እና የተከሣሽን መከራከሪያዎች ከሽያጭ ውል ምንነት፣ ባህሪይ እና አመሰራረት አኳያ በመመልከት ከቀረቡት የክፍያ ደረሰኞች ፣ ከተጠሪ ለአመልካች የተጻፈ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ እንዲሁም በፍ/ቤቱ ትዕዛዝ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በአመልካች ስም በተከፈተ የባንክ ሂሳብ አመልካች ገንዘብ ገቢ ያደረገ መሆኑን የሚያሳይ ምላሽና ማስረጃ ቀርቧል፡፡

ፍ/ቤቱ የግራቀኙን ምስክሮች አስቀርቦ የሰማ ሲሆን በከሣሽ በኩል የተሰሙት ሁለቱም ምስክሮች ክፍያው የተፈጸመው በክሱ ላይ ለተገለጸው ሲሚንቶ መሆኑን እና የሲሚንቶ አቅርቦት ስምምነት ውል የተደረገ መሆኑን በአመልካች በኩል ከቀረቡት ምስክሮች በተሻለ በመመስከራቸው በአመልካችና በተጠሪ መካከል የሲሚንቶ ሽያጭ ውል መደረጉና ተከሣሽ በውሉ መሠረት ሚፈለግበትን የሲሚንቶ ዋጋ በወቅቱ የከፈለ መሆኑ እንዲሁም ተከሣሽ በውል ግዴታው ሥረት ለከሣሽ ሽጦ ክፍያ የተቀበለበትን ሲሚንቶ ሳያስረክብ መቅረቱ ተረጋግጧል፤ ተከሣሽ ከአቅም በላይ የሆኑ ችግሮች በመከሰታቸው ምክንያት ሲሚንቶ ማስረከብ ያልቻለና ሊገደድ የማይገባ መሆኑን በመግለፅ ክርክር ቢያቀርብም ችግሮች ተከስተዋል የተባሉበት ጊዜ የውል ግዴታው መፈፀም ከነበረበት ጊዜ አንፃር ዘግይተው የተከሰቱ ከመሆኑ አኳያ የተከሣሽ ክርክር ተቀባይነት የሌለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም አመልካች 6,402 ከንታል ሲሚንቶ ለተጠሪ ሊያስረክብ ይገባል እንዲሁም ወጪና ኪሳራ በድምሩ ብር 28,446.00 (ሃያ ስምንት ሺህ አራት መቶ አርባ ስድስት ብር) ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም በስር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ ሳይለወጥ ቀርቷል፡፡ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአሁን አመልካች በቀን 12/11/2015 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ የአሁን አመልካች ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ምርት ማምረት የማልችል መሆኑን ገልጬ እና ተጠሪ ሌሎች ከ20 በላይ ሲሚንቶ ፋብሪካዎች በአገራችን ባሉበት ሁኔታ ተጠሪ ከእነሱ መግዛት እየቻለ ከሌሎች ሲሚንቶ ፋብሪካዎች የማይገዛበትን ምክንያት እንዲሁም አመልካች ተገዶ ሲሚንቶ ሊያስረክበኝ ይገባል የሚልበትን ምክንያቶች ባላስረዳበት ፣ ተጠሪ ከሚመረተው ሲሚንቶ ልዩ ጥቅም ያለዉ ስለመሆኑ በምንም ማስረጃ ባላስረዳበት ሁኔታ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ .44873 ከሰጠው የህግ ትርጉም በተቃራኒ የስር ፍ/ቤት አመልካች 6402 ኩንታል ሲሚንቶ አስረክቡ ተብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመ ስለሆነ ውሳኔው ሊታረም ይገባል፡፡ የስርመ /ደ/ፍ ቤትም ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት መኖሩን አምኖ ነገር ግን ከአቅም በላይ የሆነው ምክንያት የነበረው ክፍያ በተፈጸመ ግዜ አልነበረም በማለት ተጠሪ ክፍያ የፈጸመበትን ቀን እንደማስረከቢያ ቀን መውሰዳቸው ስህተት ሲሆን ማስረከብ የነበረብን ተጠሪ በጠየቀበት ቀን ሆኖ እያለ በዚህ ግዜ ውስጥ ደሞ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ውስጥ እንደነበር ተረጋግጦ ባለበት የስር ፍ/ቤቶች ማስረከቢያ ቀን

ክፍያ በተፈጸመበት ቀን አድርገው መቁጠራቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፤የስርመ /ደ ፍርድ ቤት ተጠሪ ወለድ እንዲከፈለዉ ዳኝነት አልጠየቀም፣ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ወለድ እንዲከፈለው ባልጠየቀበት አመልካች ወለድ እንዲከፍል መወሰኑ የፍታብሄር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 182/2/ መሰረት ባልተጠየቀ ዳኝነት የተወሰነ በመሆኑ መሰረታዊ ህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ጠይቀዋል።

ተጠሪ በሰጠው መልስ አመልካች ክፍያ በተፈጸመበት ወቅት እናም ከዛም በኋላ በነበሩት ጊዜያት ከአቅም በላይ የሆነ ችግር እንዳልነበረበት በስር ፍ/ቤት በቀረበው መረጃ ለመረዳት የተቻለ በመሆኑ በዚሁ መሰረት የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ሊነቀፍ የማይገባው ነው። በአይነት ለማስረከብ እንደ ፍርዱ እንድንፈጽም ተገደናል ፣ ተጠሪ ከአመልካች ልዩ ጥቅም ያለው መሆኑን አላስረዳም በሚል ቢያቀርብም የስር ፍ/ቤት ምንም እንኳን ከአቅም በላይ የሆነ ችግር የተፈጠረው ማስረከብ ከነበረበት ጊዜ በኋላ ቢሆንም በአፈጻጸም ወቅት እንደ አማራጭ ከሌሎች ፋብሪካዎች ቀሪውን የሲሚንቶ ክፍያ በመክፈል ተጠሪ እንዲረከብ አማራጭ መፍትሄ አስቀምጦ ከሌሎች ተመሳሳይ ፋብሪዎች ላይ ክፍያ እንዲፈጽም እና ተጠሪ እንዲረከብ የስር ፍቤት በአማራጭ ማስቀመጡ የአፈጻጸም ሂደት ሊነቀፍ የሚገባው አይደለም። ይህም የሚያመላክተው አመልካች የግድ ምርቱን በአይነት ከራሱ ፋብሪካ ብቻ እንዲያስረክብ አለመሆኑን ነው።አመልካች ሆነ ብሎ ምርት ባላቆመበት ጊዜያት ለተጠሪ ምርቱን ማስረከብ እየቻለ ተጠሪን ለከፍተኛ ኪሳራ የዳረገው በመሆኑ እንዲሁም አመልካች ግዴታቸውን መወጣት በሚችሉበት ወቅት ባለመወጣታቸው ከተጠሪ ሙሉ ክፍያ ከወሰደ በኋላ በወቅቱ ባለማስረከባቸው ማስረከብ ከሚገባቸው ጊዜ ጀምሮ የሚታሰብ ወለድ እንዲከፍሉ መወሰኑ ሊነቀፍ የሚገባው ባለመሆኑ የስር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ እንዲያጸናልን እንዲሁም በዚህ የሰበር አቤቱታ ምክንያት ላወጣናቸው ወጪዎች በቁርጥ ውሳኔ እንዲሰጥልን በማለት አቅርበዋል። አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቷል።

የግራቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው። ይህ ችሎትም ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፣ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ የተፈጸመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን እንደሚከተለው መርምሮታል። ውሳኔ የሰጠነው በተያዘው ጭብጥ ላይ በተደረገው ክርክር ነው።አመልካች ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ገጠመኝ በማለት የሚያነሳውን መከራከርያ በተመለከተ ገንዘብ በተቀበለበት ግዜም ሆነ ማስረከብ በሚገባውግዜ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር እንዳልነበረ ማስረጃ በሚያጣራው ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ነው። ይህ መዝገብ ሲያስቀርብ የተጠቀሱት የፍ/ህ/ቁ1776፣2329 እና የሰበር ውሳኔዎች የሚገልጹት ውል ተገዶ ይፈጸም ለማለት ውሉ ይፈጸምልኝ ለሚለው ወገን የተለየ ጥቅም የሚሰጥ መሆን አለበት፤በሌላ በኩል ውሉን ተገዶ በሚፈጽመው ተዋዋይ ነጻነት ላይ ችግር የሚያደርስ መሆን የለበትም የሚለውን ነው።

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመጣ አመልካች ሲሚንቶ አስረክባለሁ ብሎ ብር በተቀበለበት 2014 አ.ም የነበረው የሲሚንቶ ዋጋ እና ክሱ በቀረበበት ግዜም ሆነ አሁን ያለው ልዩነት እጅግ ከፍ ያለና ብዙ እጥፍ እንደሆነ አመልካች እራሱ ከስር ጀምሮ ባቀረበው መከራከርያ ላይ የገለጸው ነው፡፡ ስለዚህም ተጠሪ የተለየ ጥቅም እንደሚያስገኝለት አውቆ ሲሚንቶውን ለመረከብ ጠይቋል፡፡ ሲሚንቶውን በአይነት ማስረከብ በአመልካች ነጻነት ላይ የሚፈጥረው ችግር አለወይ ወደሚለው ስንመጣ ደግሞ አመልካች አሁንም ሲሚንቶ እያመረተ ያለ ድርጅት ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ሲሚንቶ አስረክብ ቢባል ነጻነቱን የሚነካ ምክንያት የለም፡፡ አመልካች በግልጽ ከስር ጀምሮ ያደርግ በነበረው ክርክር ገንዘብ መመለስ መፈለጉ እሱ ገንዘብ በወሰደ ግዜ ገንዘብ የነበረው ዋጋ አሁን በመውረዱና የሲሚንቶም ዋጋ እጅግ ከፍ በማለቱ ከዚህ ለመጠቀም እንጂ ገንዘብ የተቀበለበትን ሲሚንቶ ለማስረከብ ምንም ነጻነቱን የሚነካ ምክንያት ባለመኖሩ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም ብለን ከዚህ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

- የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 03219 በግንቦት9/2015 የወሰነውና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ306130 በሰኔ 3/2015 የፌደራል መጀመርያ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማጽናት የሰጠው ውሳኔ ተገቢ በመሆኑ በሰበር/ስ/ስ/መመርያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1)9ሀ) መሰረት አጽንተነዋል፡፡
- በዚህ መዝገብ በህዳር 17/2016 ተሰጠው እግድ ተነስቷል፡፡ እግዱ ስለመነሳቱ እግድ ለተላለፈላቸው ክፍሎች ይድረስ፡፡
- የዚህን ፍርድ ቤት ወቺና ኪሳራ ግራቀኙ ይቻቻሉ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 251399

ህዳር 26 ቀን 2017ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ብርቅነሽ እሱባለው

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች ፡- አቶ ኡመር ብሩ ናስር ጠበቃ የሰላም ዜና ቀረቡ

ተጠሪዎች ፡- 1. ወ/ሮ ነፃነት ድምሩ ገዛኸኝ አልቀረቡም

2. አቶ ፍቅርዓለም በድሉ ሃብቴ ቀረቡ

3. አቶ መሐመድ ሽምሱ አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ ከፍርድ ቤት ንብረት ለማስከበር የተሰጠ እግድ በግብይት ላይ የሚኖረውን ውጤት የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

እንደተረዳነው በሥር ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ፣1ኛ እና 2ኛ ተጠሪ ተከሳሾች ፣3ኛ ተጠሪ ጣልቃገብ ነበሩ፡፡

አመልካች ኅዳር 15 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት ክስ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ለተበደሩት ብድር ዕዳ መክፈያ እንዲሆናቸው ንብረትነቱ የ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች የሆነውን በካርታ ቁጥር ወ3/ወዝ01/845/16850/00 የሚታወቅ በአዲስ አበባ ከተማ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ወረዳ 03 የሚገኝ ይዞታ ኅዳር 18 ቀን 2010ዓ.ም በመንደር የሽያጭ ውል እና ቀጥሎ ጥቅምት 27 ቀን 2013 ዓ.ም በፌደራል የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት በመቅረብ የሽያጭ ውል ብንዋዋልም ቤቱን ነጻ አድርገው ሊያስረክቡኝ አልቻሉም፡፡ የመንደር ውሉን ከተዋዋልን በኃላ ከ3ኛ ተጠሪ ጋር በነበራቸው የገንዘብ ክርክር ምክንያት ቤቱን ለማስፈጸሚያነት ሊያደርጉት ክርክር ላይ እንዳሉ ያወቅኩ በመሆኑ በሽያጭ ውሎቹ መሰረት ንብረቱን ከማንኛውም እዳና እገዳ ነጻ አድርገው እንደያዘዋውሩልኝ፤ይህን የማያደርጉ ከሆነ ግን ስመ ሃብቱ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲዘዋወርልኝ ለኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ እና ለሚመለከተው አካል ትዕዛዝ ይሰጥልኝ ሲሉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በሰጡት መልስ አመልካች በክሳቸው የጠቀሱትን የሽያጭ ውሎች አድርገናል የሽያጭ ገንዘቡንም ተቀብለናል ነገር ግን የሦስተኛ ወገኖችን ጣልቃ ገብነት ልናስቆም የማንችል በመሆኑ ፍ/ቤቱ ለኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ሆነ ለሌላ የሚመለከተው አካል ትዕዛዝ ቢሰጥ አንቃወምም በማለት አቅርበዋል፡፡ 3ኛ ተጠሪ የጣልቃገብ አቤቱታ እንዲያቀርቡ ከተፈቀደላቸው በኃላ በሰጡት መልስ ከቼክ ጋር በተገናኘ በ2ኛ ተጠሪ ላይ በመ/ቁጥር 220021 ክስ አቅርቤ ኅዳር 25 ቀን 2011ዓ.ም ተፈርዶበታል፡፡ በክርክሩ ወቅትም ኅዳር 17 ቀን 2011 ዓ.ም የተጠቀሰው ቤት እንዲታገድ ትዕዛዝ ተሰጥቶ ነበር፡፡ አፈጻጸም በመ/ቁጥር 224343 ተከፍቶ በቤቱ ላይም በጨረታ እንዲሸጥ ትዕዛዝ የወጣበት በመሆኑ ለ3ኛ ወገን የሚተላለፍበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ አመልካች ቤቱ መታገዱን ያውቃል፡፡ ኅዳር 18 ቀን 2010 ዓ.ም ያደረገው የቤት ሽያጭ ውል ያልተመዘገበ በመሆኑ በ3ኛ ወገን ላይ ተፈፃሚነት የለውም፡፡ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ በሰጠው ውሳኔ አመልካች ከ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪ ጋር ኅዳር 18 ቀን 2010ዓ.ም ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል ስምምነት ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት ቀርቦ ያልተመዘገበ በመሆኑ በሕግ ፊት የሚፀና ውል፤ አይደለም፡፡ ጥቅምት 27 ቀን 2013ዓ.ም ተደረገ የተባለው የቤት ሽያጭ ውልም የተደረገው ሕዳር 17 ቀን 2011ዓ.ም በፍ/ቤት እግድ ከተሰጠበት እና የካቲት 29 ቀን 2011ዓ.ም የፌ/ከ/ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 224343 ቤቱ በሃራጅ እንዲሸጥ ትዕዛዝ ከተሰጠበት በኃላ በመሆኑ በሕግ ፊት የሚፀና ውል አይደለም በማለት አመልካች የቤቱ ስመ ሃብት እንዲዘዋወርላቸው ያቀረቡትን ጥያቄ ውድቅ አድርጎታል፡፡የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበውን ይግባኝ በአብላጫ ድምጽ ባለመቀበል ሰርዟል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ አመልካች በ24/11/2015 ዓ/ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን ይዘቱም፡- የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክር ያልቀረበበትን እና ዳኝነት ያልተጠየቀበትን ነጥብ በመያዝ የሽያጭ ውሉ በታገደ ቤት ላይ የተደረገ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡ የስር ፍ/ቤት በውሳኔው የሚጠቅሰው ግንቦት 6 ቀን 2011 ዓ.ም ክፍለ ከተማው የጻፈው ደብዳቤ ይዞታው ለሕብረት ባንክ ብድር መያዣነት መታገዱን እንጂ ለተጠሪ የታገደ መሆኑን አያሳይም፡፡ የሥር ፍ/ቤት ተጠሪ ከግዢው በፊት ቤቱን ለፍርድ ማስፈጸሚያ አሳግደውታል ወይ የሚለውን ነጥብ በአግባቡ ሳያጠራ ውሳኔ በመስጠቱ የሥነ ሥርዓት ሕግ ጥሰት የተፈጸመበት ነው፡፡ በፍ/ቤት የተሰጠ እግድ መኖሩ ቢረጋገጥ እንኳን በማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ ላይ እስካልተመዘገበ ድረስ በ3ኛ ወገን ላይ አስገዳጅነት የለውም፡፡ የእግዱ ትእዛዝም ቢሆን ለ3ኛ ተጠሪ የቀዳሚነት መብት ከሚሰጣቸው በስተቀር በጽሁፍ የተደረገና የተመዘገበን የሽያጭ ውልን ዋጋ የለውም ለማለት የሚያስችል የህግ መሰረት የለም፡፡አመልካች ቤቱን የገዙት ከእዳ ነጻ የሚል የጀርባ መሃተም ከኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ አስመትተው በመሆኑ እና ክፍለ ከተማው ሁለት የይዞታ ማረጋገጫ የካርታ ቁጥር በመስጠቱ የስር ፍ/ቤት የኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማውን የክርክሩ አካል ማድረግ ሲገባው ሳያደርግ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊሻር ይገባል የሚል ነው፡፡

ሰበር ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ አንድ ፍርድ መሰጠት የሚገባው ከግራ ቀኝ በተጠየቀው ጉዳይ ስለመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 182(2) የተደነገገ ከመሆኑ አንጻር የሥር ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍርዱ ማጠቃለያ ላይ ለክርክር ምክንያት በሆነው ቤት ላይ የተደረገው ውል በሕግ ፊት የሚፀና ውል አለ ለማለት አይቻልም ያለበት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎትም ቅሬታውን የሰረዘበትን አግባብ ከግራ ቀኝ የቀረበውን የዳኝነት ጥያቄ መሠረት ያደረገ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀርቡ አዟል፡፡

1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በ20/03/2016 ዓ/ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ የስር ፍ/ቤት ከቀረበው ክርክር አንጻር የሽያጭ ውል ከመፈጸሙ በፊት የቀደመ የፍ/ቤት የእግድ ትዕዛዝ እንዳለበትና ሽያጩም የተከናወነው ይህ እግድ ትዕዛዝ ተጥሶ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ ከተከራካሪ ወገኖች ከቀረበው ክርክር አንጻር እና ከክፍለ ከተማው ከቀረበው የሰነድ ማስረጃ አንጻር በመመርመር በመሆኑ ምንም አይነት መሰረታዊ የህግ ስህተት አልተፈጸመበትም የሚል ነው፡፡

3ኛ ተጠሪ በ20/03/2016ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ የአመልካች ቅሬታ የማስረጃ ምዘናን የሚመለከት በመሆኑ በሰበር ሰሚ ችሎት ሊታይ አይገባም፡፡ አመልካች ሁለቱን ውሎች መሰረት አድርገው 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪ ቤቱን እንዲያስረክቧቸው ወይም የቤቱ ስመሃብት እንዲዛወርላቸው ዳኝነት ሲጠይቁ ህዳር 18 ቀን 2010ዓ.ም የተደረገው ውል በሰነዶች ማረጋገጫ ምዝገባ ጽ/ቤት ያልተረጋገጠና ያልተመዘገበ ውል ነው በማለት እና ጥቅምት 27 ቀን 2013ዓ.ም የተደረገው ውልም የተፈጸመው በከፍተኛ ፍ/ቤት እግድ

ከተሰጠበት ህዳር 17 ቀን 2011ዓ.ም በኃላ በመሆኑ ውሉ የሕግ መሰረት የለውም የሚል ክርክር ያቀረብን በመሆኑ ክርክር እንዳልተደረገ ሊቆጠር አይገባም፡፡ጉዳዩ በአፈጻጸም ደረጃ ላይ እንዳለ ከ3ኛ ተጠሪ ጋር አመልካች ድርድር እያደረጉ የነበረ በመሆኑ ስለእግዱ ያውቁ ነበር በሚል በስር ፍ/ቤት አመልካች ክርክር ሲያቀርቡ አመልካች የማስተባበያ ክርክር አላቀረቡም፡፡ንብረቱ በከፍተኛ ፍ/ቤት ከታገደ በኃላ የኮ/ቀ/ክ/ከ/አስተዳደር የይዞታ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ ፕሮጀክት ጽ/ቤትም እንደ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ያገደ መሆኑን ህዳር 18 ቀን 2011ዓ.ም ለፍ/ቤቱ በጻፈው መልስ ያሳወቀ በመሆኑ ተገቢ ማጣራት አልተደረገም ሊባል አይችልም፡፡ ፍ/ቤቱ በክ/ከተማው የሚገኝ የታገደው ንብረት ዋና ማህደር አስቀርቦ የእግድ ትዕዛዙ በማህደሩ ውስጥ መኖሩን ያረጋገጠ በመሆኑ አመልካች በማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ ላይ አልተመዘገበም በሚል ያቀረቡት ክርክር ተገቢነት የለውም፡፡ ክፍለ ከተማው በሰጠው በሁለቱም ካርታ የካርታ ቁጥር ሴሪ ተመሳሳይ ስለሆነ ሁለት የተለያዩ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ቁጥር አለው አያስብልም፡፡ አመልካች በስር ፍ/ቤትም ይህንን ክርክር አላነሱትም የሚል ነው፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የግራቀኙን ክርክር፣ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ እና ሕጉን መነሻ በማድረግ ውሳኔው ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አመልካች ኅዳር 15 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት ክስ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ለተበደሩት ብድር ዕዳ መክፈያ እንዲሆናቸው ንብረትነቱ የ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች የሆነውን በካርታ ቁጥር ወ3/ወዝ01/845/16850/00 የሚታወቅ በአዲስ አበባ ከተማ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ወረዳ 03 የሚገኝ ይዞታ ኅዳር 18 ቀን 2010 ዓ.ም በተለምዶ የመንደር የሽያጭ ውል ተብሎ በሚገለጸው እና ቀጥሎ ጥቅምት 27 ቀን 2013 ዓ.ም በፌደራል የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት በመቅረብ የሽያጭ ውል ብንዋዋልም ቤቱን ነጻ አድርገው ሊያስረክቡኝ አልቻሉም፡፡ የመንደር ውሉን ከተዋዋልን በኂላ ከ3ኛ ተጠሪ ጋር በነበራቸው የገንዘብ ክርክር ምክንያት ቤቱን ለማስፈጸሚያነት ሊያደርጉት ክርክር ላይ እንዳሉ ያወቅኩ በመሆኑ በሽያጭ ውሎቹ መሰረት ንብረቱን ከማንኛውም እዳና እገዳ ነጻ አድርገው እንደያዘዋውሩልኝ፤ ይህን የማያደርጉ ከሆነ ግን ስመ ሃብቱ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲዘዋወርልኝ ለኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ እና ለሚመለከተው አካል ትዕዛዝ ይሰጥልኝ ሲሉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ክሱን አምነው የተከራከሩ ሲሆን 3ኛ ተጠሪ በክርክሩ ጣልቃ በመግባት ከቼክ ጋር በተገናኘ በ2ኛ ተጠሪ ላይ በመዝገብ ቁጥር 220021 ክስ አቅርቤ ኅዳር 25 ቀን 2011 ዓ.ም ተፈርዶበታል፡፡ በክርክሩ ወቅትም ኅዳር 17 ቀን 2011ዓ.ም የተጠቀሰው ቤት እንዲታገድ ትዕዛዝ ተሰጥቶ ነበር፡፡ አፈጻጸም በመዝገብ ቁጥር 224343 ተከፍቶ በቤቱ ላይም በጨረታ እንዲሸጥ ትዕዛዝ የወጣበት በመሆኑ ለ3ኛ ወገን የሚተላለፍበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ አመልካች ቤቱ መታገዱን ያውቃል፡፡ ኅዳር 18 ቀን 2010 ዓ.ም ያደረገው የቤት ሽያጭ

ውል ያልተመዘገበ በመሆኑ በ3ኛ ወገን ላይ ተፈፃሚነት የለውም፡፡ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ በሰጠው ውሳኔ አመልካች ከ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪ ጋር ኅዳር 18 ቀን 2010 ዓ.ም ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል ስምምነት ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት ቀርቦ ያልተመዘገበ በመሆኑ በሕግ ፊት የሚፀና ውል አይደለም፡፡ ጥቅምት 27 ቀን 2013 ዓ.ም ተደረገ የተባለው የቤት ሽያጭ ውልም የተደረገው ሕዳር 17 ቀን 2011 ዓ.ም በፍርድ ቤት እግድ ከተሰጠበት እና የካቲት 29 ቀን 2011 ዓ.ም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮምፒውተር መዝገብ ቁጥር 224343 ቤቱ በሃራጅ እንዲሸጥ ትዕዛዝ ከተሰጠበት በኋላ በመሆኑ በሕግ ፊት የሚፀና ውል አይደለም በማለት አመልካች የቤቱ ስመ ሃብት እንዲዘዋወርላቸው ያቀረቡትን ጥያቄ ውድቅ አድርጎታል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረቡትን ይግባኝ በአብላጫ ድምጽ ባለመቀበል ሰርዟል፡፡

ክርክሩን በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሰረት መምራት እና መቆጣጠር የፍርድ ቤቱ ኃላፊነት ሲሆን በተገቢው ሁኔታ ካልተመራ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ዓላማዎች የሆኑትን እንደ አንጻራዊ እውነትን የመፈለግ፣ ሥነ-ሥርዓታዊ ፍትህ፣ ክርክርን ውጤታማ፣ ወጭና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ መምራት የመሳሰሉትን ማሳካት ስለማይቻል የተከራካሪዎችን መብት ይነካል፡፡ ክርክር የሚወሰነው በተጠየቀው ዳኝነት አግባብ እንደሆነ የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 182(2) ላይ ተመልክቷል፡፡ ፍርድ ቤቱም ከቀረበው ዳኝነት አኳያ ከግራቀኙ ክርክር በመነሳት በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 246 እና ተከታዮቹ መሠረት በተነሱት ጉዳዮች ጭብጥ መስርቶ ውሳኔ የመስጠት ኃላፊነት አለበት፡፡

3ኛ ተጠሪ ንብረቱ እንዲታገድ ያደረጉት የፍርድ ባለመብት ቢሆኑ ፍርዱ የሚፈጸምበት ንብረት እንዳያጡ ለማስከበር የተደረገ በመሆኑ ጉዳዩ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 151-153 የተመለከተው ከፍርድ በፊት ንብረት ተከብሮ እንዲቆይ (attachment) የሚደረግበትን ሥርዓትና ሁኔታ የሚመለከት ነው፡፡ ከፍርድ በፊት ንብረት ስለማስከበር በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 151 ላይ የተመለከተዉ ተከሳሽ የሆነ ወገን ክሱን ለማሰናከል ያቀደ መሆኑ ወይም የተሰጠዉ ትዕዛዝ እንዳይፈጸም ዘዴ መፍጠሩ ከሳሽ ለፍርድ ቤቱ በሚያቀርበዉ ቃለ መሃላ ከተረጋገጠ እና ተከሳሹ ንብረቱን በሙሉ ወይም በከፊል ለማሸሽ ወይም ለማባከን ማቀዱን ወይም ንብረቱን በሙሉ ወይም በከፊል ክሱ ከቀረበበት ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣን ክልል ዉጪ ለማሸሽ ማቀዱን ፍርድ ቤቱ የተረዳ እንደሆነ እና የሚጠየቀዉን ዋስትና ያላቀረበ እንደሆነ ንብረቱ ተከብሮ እንዲቆይ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ መስጠት የሚችል መሆኑን የሚያስገነዝብ ነዉ፡፡ በዚህ መልኩ የሚሰጥ የንብረት ማስከበር ትዕዛዝ ህጋዊ ዉጤት በሕጉ አንቀጽ 153 ላይ የተመለከተዉ ሲሆን በዋነኛት ከሳሽ ለሆነው ወገን የተፈረደለት እንደሆነ፣ ከሳሹ ለፍርዱ አፈፃፀም ንብረት እንዲከበር ሌላ ማመልከቻ ማቅረብ ሳያስፈልግ አፈፃጸሙ በተያዘዉ ንብረት ላይ እንዲቀጥል ማድረግ የሚያስችል፣ እግዱ ንብረትን የመከታተል መብት (right in

rem) የሚሰጥ በመሆኑ እግድ ከተሠጠ በኋላ የተደረጉ የንብረት ሀብትነት ማስተላለፍ ተግባሮች (consequent transactions) ንብረቱን ባሳገደው ሰው ላይ ውጤት የላቸውም፡፡

በዚህ ረገድ የሥር ፍርድ ቤቶች 3ኛ ተጠሪ ንብረቱን ማስከበራቸውን መሠረት በማድረግ ንብረቱ ከታገደ በኋላ አመልካች በውል አዋዋይ ፊት ያደረጉት የሽያጭ ውል 3ኛ ተጠሪ ላይ ውጤት የሌለው በመሆኑ በአፈጻጸም ክርክር መብታቸውን የሚያስከብሩበት እንጂ ንብረቱ 3ኛ ወገን ወደሆኑት አመልካች ሥመ-ሀብቱ ሊዛወር አይገባም በማለት ክሱን ውደቅ ማድረጋቸው ሕጉን የተከተለ ነው፡፡

በሌላ በኩል ክርክር የሚወሰነው በተጠየቀው ዳኝነት አግባብ እንደሆነ የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 182(2) ላይ ተመልክቷል፡፡ በሥር ፍርድ ቤት በተደረገ ክርክር ገዥ እና ሻጭ የሆኑት አመልካች እና 1ኛና 2ኛ ተጠሪዎች ሽያጭ ውል ስለመኖሩ ተማምነዋል፡፡ በመካከላቸው የጸና ውል ስለመኖሩ ባልተካካዱበት የሥር ፍርድ ቤቶች የጸና ውል የለም በማለት የደረሱበት መደምደሚያ የግራቀኙን ክርክር መሠረት ያላደረገና መሠረታዊ የሆነ የክርክር አመራር ሥርዓት ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 242796 ሰኔ 28 ቀን 2015 ዓ/ም እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 262290 ታህሳስ 25 ቀን 2015 ዓ/ም የሰጡት ውሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1(ሀ) መሠረት ከ3ኛ ተጠሪ መብት አንጻር የአመልካች ክስን ውድቅ በማድረግ የሰጡት ውሳኔ በውጤቱ ጸንቷል፡፡

2. በዚህ ችሎት ግራቀኙ ያወጡትንና ወጭና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

- ውሳኔው ለሥር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- ውሳኔው ታህሳስ 02 ቀን 2017 ዓ/ም በችሎት ተነቧል፡፡
- በዚህ ችሎት ነሀሴ 01 ቀን 2015 ዓ/ም የተሰጠው እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መዝገብ ቁጥር - 252106

ቀን -30/03/2017ዓ/ም

ዳኞች - ሽመክት አሰፋ

እንዳሻው አዳነ

አለማየሁ ሹናራ

ተናኘ ጥላሁን

ዘውዲቱ ታደሰ

አመልካች - ህዳሴ ቴሌኮም አክስዮን ማህበር ነገረ ፈጅ ብርሃኑ መንገሻ ቀረቡ

ተጠሪ - አቶ ዳዊት ጂሬኛ አልቀረቡም

መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው ለምርመራ ስለሆነ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የተጀመረው በምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች ተከሳሽ የአሁን ተጠሪ ከሳሽ የነበሩ ሲሆን ከሳሽ ባቀረቡት ክስ በተከሳሽ መስሪያ ቤት ሲሰሩ በመዝገብ ቁጥር 56212 ተከሰው ከተለያዩ ወጪዎች ጋር ብር 65,160.19 (ስልሳ አምስት ሺህ አንድ መቶ ስልሳ ብር ከአስራ ዘጠኝ ሳንቲም) የተወሰነባቸውና ለዚህም ማስፈፀሚያ እንዲሆን የብር 107,591.38 (አንድ መቶ ሰባት ሺህ አምስት መቶ ዘጠና አንድ ብር ከሰላሳ ስምንት ሳንቲም) አክስዮን ድርሻቸው ላይ ጨረታ የወጣ ቢሆንም የሚገዛ ሰው በመታጣቱ ካላቸው የአክስዮን ድርሻ ላይ ብር 65,160.19 (ስልሳ አምስት ሺህ አንድ መቶ ስልሳ ብር ከአስራ ዘጠኝ ሳንቲም) ተቀንሶ የተከፈለ ስለሆነ ቀሪው የብር 42,631.19 (አርባ ሁለት ሺህ ስድስት መቶ ሰላሳ አንድ ብር ከአስራ ዘጠኝ ሳንቲም) አክስዮን ድርሻ በገንዘብ እንዲከፈለኝ በማለት ክስ ያቀረቡ ሲሆን

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ይህም ክስ ለተከሳሽ ደርሶ ተከሳሽ የተሻሻለ መልሳቸውን አቅርበዋል የመልሳቸውም ይዘት ከሳሽ በተከሳሽ ድርጅት ውስጥ የአክስዮን ድርሻ ያላቸው ሲሆን ይህንንም የአክስዮን ድርሻ በንግድ ህጉ መሰረት በየአመቱ በድርሻቸው መጠን መክፈል፣ ለ 3ኛ ወገን ማስተላለፍ እና በጨረታ መሸጥ እንጂ ማህበሩ መክሰሩን አውጆ ባልፈረሰበት ሁኔታ ከሳሽ ያለውን የአክስዮን ድርሻ በገንዘብ ተቀይሮ እንዲከፈላቸው የመጠየቅ መብት የሌላቸው በመሆኑ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት የተሻሻለ መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም ከሳሽ ከተከሳሽ ማህበር ውስጥ ብር 42,631.19 (አርባ ሁለት ሺህ ስድስት መቶ ሰላሳ አንድ ብር ከአስራ ዘጠኝ ሳንቲም) ያላቸው መሆኑን ተከሳሽ አምነዋል፡፡ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 40 መሰረት ባለንብረት በንብረቱ የመጠቀም መብት ያለው በመሆኑ ተከሳሽ በቆጠቡት ገንዘብ ለመጠቀም የሚከለክላቸው ነገር ስለሌለ ተከሳሽ ለከሳሽ የቆጠቡትን ብር 42,631.19 (አርባ ሁለት ሺህ ስድስት መቶ ሰላሳ አንድ ብር ከአስራ ዘጠኝ ሳንቲም)፣ የዳኝነት ክፍያ ብር 1,593.00 (አንድ ሺህ አምስት መቶ ዘጠና ሶስት ብር)፣ የጠበቃ አበል 15 በመቶ፣ የተለያዩ ወጪዎች ብር 500 (አምስት መቶ ብር) እንዲከፍሉ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህም ቅር በመሰኘት ተከሳሽ ወይም የአሁን አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የቀረበውን የይግባኝ አቤቱታ አያስቀርብም በማለት ሰርዞታል፡፡

የአሁን አመልካች በዚህ ቅር በመሰኘት ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በቀን 01/12/2015 ዓ.ም የተፃፈ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በአዋጅ ቁጥር 1243/2013 የንግድ ህግ አንቀፅ 473(1)(ሐ) ከተከፈለው 3/4ኛው ከቀነሰ ማህበሩ እንደሚፈርስ የሚደነግግ ሲሆን የስር ፍ/ቤቶች በሰጡት ውሳኔ መሰረት አመልካች ክፍያዎችን የሚፈጽም ከሆነ አክስዮን ማህበሩ በጤናማ ሁኔታ የሚገኝ ቢሆንም በሕጉ መሰረት የሚፈርስ ከመሆኑም በላይ ውሳኔውን እንደምሳሌ (precedent) በመውሰድ ሌሎች በአክሲዮን በተቋቋሙ ኩባንያዎችን ህልውና አደጋ ላይ የሚጥል በመሆኑ ሊታረም ይገባል፡፡ እንዲሁም ከአንቀጽ 473 እስከ 491 እና በአመልካች መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 28 እና 29 ድንጋጌዎች መሰረት አክሲዮን ማህበር በምን ሁኔታ እንደሚፈርስና ውጤቱ ምን እንደሆነ የሚደነግግና ተቀንሶ ቢከፈል ማህበሩ የሚፈርስና ማህበሩ ቢፈርስ በንግድ ሕጉ አንቀጽ ከ 483 እስከ 485 መሰረት የተደነገጉትን የገንዘብ ጠያቂዎችን መብት ጥበቃ የሚቃረን ነው፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች አግባብ ካለው ሕግ ጋር ሳይመረምሩ አክሲዮኑ በገንዘብ ተቀይሮ ሊከፈለው ይገባል በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው፡፡ ተጠሪ በአመልካች ድርጅት ውስጥ አክሲዮን በመግዛት ያፈሩት ንብረት ምንም እንኳን ሕገ መንግስታዊ መብት ቢሆንም ዝርዝር አፈጻጸማቸው ግን በንግድ ሕግ እና ተጠሪ ወደውና ፈቅደው በአፀደቁት የመተዳደሪያ ደንብ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የስር ፍርድ ቤቶች አግባብነት የሌለውን ህግ በመጥቀስ ውሳኔ መስጠታቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ ሊሻር ይገባል በማለት አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም የቀረበውን የሰበር አቤቱታ ከስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ጋር አጣምሮ በመመርመር ተጠሪ በአመልካች ማህበር ውስጥ አላቸው የተባለው የብር 42,631.19 (አርባ ሁለት ሺህ ስድስት መቶ ሰላሳ አንድ ብር ከአስራ ዘጠኝ ሳንቲም) አክሲዮን ድርሻ በገንዘብ ተቀይሮ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍሉ መወሰኑ

ህጉን የተከተለ አይደለም በሚል የቀረበውን ቅሬታ ለማጣራት ያስቀርባል የተባለና ይህም ለተጠሪ የደረሰ ቢሆንም ተጠሪ መልሳቸውን ያላቀረቡ በመሆኑ መልስ የማቅረብ መብታቸው በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ አንቀፅ 199 መሰረት ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ በተገለፀው መሰረት በመጠቃለሉ እኛም ለሰበር ቅሬታ መነሻ የሆነውን ፍርድ፣ በግራ ቀኙ በኩል የቀረበውን ክርክር ከሰበር ማስቀረቢያ ነጥብ አንፃር ተጠሪ በአመልካች ማህበር ውስጥ ያላቸው ብር 42,631.19 አክስዮን ድርሻ በገንዘብ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍሉ የመወሰኑ አግባብነት በጭብጥነት ይዘን አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር አገናዝበን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

መርምረን እንደተረዳነው ከሆነ የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ በአክስዮን ማህበር ውስጥ ያለው ድርሻ ብር 107,591.38 ሲሆን ከዚህ ውስጥ ለማህበሩ ብር 65,160.19 ተቀንሶ ተከፍሏል ቀሪ ብር 42,631.19 ስለሚቀር ይህ ገንዘብ እንዲሰጠኝ የሚል ነው፡፡ አመልካች ገንዘቡን ለተጠሪ ከከፈለን ከ 3/4ኛ በታች ስለሚሆን ማህበሩን ማፍረስ ስለሚሆን ገንዘቡን ልንከፍል አንችልም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ በማህበሩ ውስጥ ያለውን ድርሻ መውሰድ ህገ መንግስታዊ መብቱ ስለሆነ አመልካች እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡ የአመልካች ቅሬታ ለተጠሪ ገንዘብን የምንከፍል ከሆነ ¾ ከቀነሰ ማህበሩ እንዲፈርስ የሚያደርግ ስለሆነ ማህበሩ መፍረሱ በሌሎች 3ኛ ወገኖች ላይ ጉዳት የሚያመጣ ስለሆነ ለተጠሪ እንዲከፈል መወሰኑ አግባብ አይደለም በማለት የንግድ ህግ አንቀፅ 473(1)(ሐ) ጠቅሰው ይከራከራሉ፡፡ የተሻሻለው የንግድ ህግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 አንቀፅ 473(1)(ሐ) ስር ማህበሩ የዋና ገንዘቡን ሶስት አራተኛ በኪሳራ ሲያጣ ማህበሩ እንደሚፈርስ ይደነግጋል፡፡ አንድ የአክስዮን ማህበር አባል ከማህበሩ ለመውጣት በሚፈልግበት ጊዜ አክስዮን ድርሻውን ለሌላ 3ኛ ሰው በመሸጥ ሊወጣ ይችላል፡፡ የተጠሪ ድርሻ የማህበሩ አባላት ወይም የውጪ ሰው የመግዛት መብት አላቸው፡፡ የማህበሩ አባላት መካከል አንዱ አባል ወይም ሁሉም አባላት ከገዙ የማህበሩ ድርሻ ይጨምራል፡፡ ማህበሩ የተጠሪን ድርሻ ከፍሎ አክስዮን ድርሻውን ማሳደግ ማህበሩ እንዲፈርስ ሊያደርግ አይችልም፡፡ አመልካች የካፒታል መጠኑ ምን ያህል እንደሆነ ግልፅ አድርጎ አልተከራከረም፡፡ የተጠሪ ድርሻ ብር 42,631 መቀነስ ማህበሩን ከ ¾ በታች ያደርጋል ተብሎ ሊገመት አይችልም፡፡ በመርህ ደረጃ የማህበሩ አባል ሲለቅ ድርሻውን ለሌላ ወገን አስተላልፎ መውጣት የሚችል ሲሆን የተጠሪን ድርሻ የሚገዛ ሌላ 3ኛ ወገን በሚጠፋበት ጊዜ ተጠሪ ገንዘቡን ለማህበሩ ትቶ እንዲወጣ ማድረግ ለህሊና የሚከብድና ፍትህን የሚያዛባ በመሆኑ ተጠሪ ከማህበሩ ድርሻውን ገንዘብ እንዲወስድ መወሰኑ ስህተት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የንግድ ህጉ ማህበር በሚፈርስበት ጊዜ ከማህበሩ ገንዘብ ጠያቂዎች መብትን በተመለከተ ጥበቃ የሚያደርግ ሲሆን አሁን በያዝነው ጉዳይ አመልካች ለተጠሪ ድርሻውን ገንዘብ ሲከፍል ¾ ኪሳራ ውስጥ የሚጥል ስለመሆኑ አመልካች በማስረጃ አላስረዳም፡፡ አመልካች ከተጠሪ የሚፈለገውን ገንዘብ ብር 65,160.19 ሲቀበል 3/4ኛ ተቀንሷል ሲል ያልተከራከረ አመልካች ለተጠሪ

እንዲከፍል በሚወሰንበት ጊዜ 3/4ኛ እንዲቀንስ ያደርጋል ይህ ደግሞ ማህበሩን ማፍረስ ነው በማለት ያነሳው ክርክር ተአማኒነት ያለው ሆኖ አላገኘንም፡፡

ሲጠቃለል ለተጠሪ ቀሪ ድርሻ ገንዘብ ብር 42,631.00 አመልካች መክፈሉ ማህበሩን የሚያፈርስ ስለመሆኑ አመልካች ያላስረዳ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት የተጠሪ ድርሻ ማህበሩ እንዲከፍል በመወሰኑ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 60738 በቀን 25/08/2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 427005 በቀን 21/09/2015 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት ባለመኖሩ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስነ ስርአት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንፅ 9(1)(ሀ) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠ እግድ ካለ ተነስቷል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነ ድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገ ለግልም!

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

**የሰ/መ/ቁ 253546**

**ህዳር 27 ቀን 2017ዓ/ም**

ዳኞች፡- ሽመክት አሰፋ

እንዳሻው አዳነ

አለማየሁ ሹናራ

ተናኜ ጥላሁን

ዋዚሞ ዋሲራ

**አመልካች፡-** በፌደራል ጉምሩክ ኮሚሽን የድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት

**ተጠሪ፡-**ሆደን የእንስሳት እርባታ ኮፖሬቲቭ ጠበቃ አጥሉ ሀብታሙ

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍርድ**

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካችመስከረም 21 ቀን 2016ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የሱማሌ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 05-1-339/15 ሰኔ 29 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ ካሳን የሚመለከት ሆኖ ክርክሩ የተጀመረው በሱማሌ ክልል የሲቲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት አመልካች ተከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ ሆነው ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ ጥር 23 ቀን 2015ዓ.ም ለሲቲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተጻፈ ክስ ተጠሪ በሱማሌ ክልል የተመዘገበ የእንስሳት ንግድ ፍቃድ ያላቸው መሆኑን በመግለጽ ተጠሪ ለሽያጭ ያቀረባቸው በጎች በድሬዳዋ ከተማ ለመሸጥ ፈልጎ የበግ ዋጋ በመቀነሱ በደንባል ወረዳ ቢዮ ኩሉል ለማቆየት በመገደዳቸው ከሀገሪቱ

**ማስታወሻ፡** - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ድንበር 100 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ለግጦሽ በተሰማሩበት አመልካች 258 የሚሆኑ በጎችን ከህግ አግባብ ውጭ የወሰደባቸው መሆኑን በመጥቀስ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.129430 እንስሳት በተያዙበት ቦታ በሚገኘው ፍርድ ቤት ስልጣን እንዳለው ውሳኔ የሰጠ በመሆኑ እና እንስሳቱ የተያዙበት ቦታ የሚገኘው ፍርድ ቤት የሲቲ ክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሆኑ ፍርድ ቤቱ የበጎቹን ዋጋ የሰራተኞችን ወጪ ጨምሮ ብር 2,388,486 ካሳ አመልካች እንዲከፍላቸው እንዲወስላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች ጥር 30 ቀን 2015ዓ.ም በሰጠው መልስ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም፤ተጠሪ በውርስ ውሳኔው ላይ ቅሬታ ካላቸው በጉምሩክ አዋጅ 859/2006 አንቀጽ 153-155 መሠረት ቅሬታ ለአመልካች ማቅረብ ነበረባቸው የሚል መቃወሚያ እና አመልካች የውርስ ውሳኔ የሰጠው በህግ የተሰጠውን ስልጣን መሰረት በማድረግ ነው የሚል የፍሬ ነገር ክርክር አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የአመልካችን መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ የግራቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኃላ አመልካች ሥልጣኑን አላግባብ በመጠቀም የተጠሪን በጎች ከድንበር በ80 ኪ.ሜ ርቀት ላይ በህገ-ወጥ መንገድ የያዘ በመሆኑ ብር 2,115,600 ካሳ ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድቤት ይግባኛቸውን ያቀረቡ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ግራቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኃላ የስር ፍ/ቤት ውሳኔን አጽንቶታል፡፡

አመልካች መስከረም 21 ቀን 2016 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይህን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ሲሆን ይዘቱም ተጠሪ በጉምሩክ አዋጅ 859/2006 አንቀጽ 153-155 መሰረት አስተዳደራዊ ሂደቱን ተከትሎ ቅሬታውን ባላቀረበበት ቀጥታ ፍርድ ቤት ቀርቦ ጉዳዩ ሊታይ እንደማይገባ ያቀረቡትን መቃወሚያ ውድቅ መደረጉ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 97372 ከሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ ውጭ መሆኑን፤ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.129430 ላይ በሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ መሰረት የቁም እንስሳት ግብይትን በሚመለከት በአካባቢው በሚገኘው ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ነው ጉዳዩ ሊታይ የሚገባው የሚባል ቢሆን እንኳን ውሳኔው በጠባቡ ተተርጉሞ በክልሉ ነዋሪዎች እና ተቋማት መካከል በሚነሱ ክርክሮች ላይ ሊተገበር የሚገባ እንጂ በፌደራል ተቋማት ላይ ተፈጻሚ ሊሆን የማይገባው መሆኑን፤ አመልካች የፌደራል ተቋም በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 3(ለ) እና አንቀጽ 5(1)(ረ) ጉዳዩን ሊያይ የሚገባው በክልሉ ያለው የፌደራል ፍርድ ቤት እንጂ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አለመሆኑን፤ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶችን በክልሎች ላይ ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 322/1995 አንቀጽ 2 የሱማሌ ክልልን ጨምሮ በአምስት ክልሎች የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በማቋቋሙ የክልሉ ፍርድ ቤት የተሰጠውን የውክልና ስልጣን ያጣ መሆኑን፤አመልካች በህግ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ስራውን በሚያከናውንበት ወቅት የሚሰጣቸው ውሳኔዎች በህግ አግባብ የሚለወጥ በመሆኑ ውሳኔው ሲሻር የተወሰደው ንብረት እንዲመለስ ይደረጋል እንጂ በካሳ ህግ መሰረት የጉዳት ካሳ ሊከፍል የማይገባ መሆኑን፤

የካሳ ክፍያው የተጠቀሱት የበጎች ብዛት፣ተመሳሳይ ዋጋ ስለማውጣት አለማውጣታቸው ባልተረጋገጠበት በተመሳሳይ ግምት የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ በሰበር ችሎት ተመርምሮ የሶማሌ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና የሲቲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን የሥረ ነገር ሥልጣን ያላቸው መሆን አለመሆኑን ከጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 153 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች እንዲሁም አዋጅ ቁጥር 322/1995 አንቀጽ 2 እና በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 97372፣129430 ከተሰጠው ትርጉሞች አንጻር አጣርቶ ለመወሰን የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

ሐምሌ 23 ቀን 2016 ዓ.ም ተጽፎ የቀረበው የተጠሪ መልስ ይዘትም አመልካች አስተዳደራዊ ውሳኔ መስጠት የሚችለው ቀረጥና ታክስ የማጭበርበር ተግባርን በሚመለከት እንጂ ከውል ውጪ ኃላፊነት ህግን በሚመለከት ውሳኔ እንዲሰጥ ስልጣን ያልተሰጠው መሆኑን፤ የስር ፍ/ቤቶች በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግሥት አንቀጽ 78(2) እና 80(2)፣(4) እና (5) መሠረት እንዲሁም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.54577 እና 20465 በሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ መሠረት በተሰጣቸው ሥልጣን መሰረት የሰጡት ውሳኔ በመሆኑ አመልካች በዚህ አግባብ ያነሱት ቅሬታ ተገቢነት የሌለው መሆኑን፤ አመልካች ከበጎቹ ብዛት እና ዋጋ ጋር ያነሱት ክርክር የፍሬ ነገር ክርክር በመሆኑ ቅሬታቸው ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን የሚያጠናክር ነሐሴ 09 ቀን 2016 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገቡ ጋር እንዲያያዝ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ፣ ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እና ቅሬታው ለሰበር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ነጥብ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደሚቻለው ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ በድሬዳዋ ከተማ በሽያጭ ለማዋል በደንባል ወረዳ ቢዩ ክልል ተሰማርተው የነበሩትን በጎች አመልካች በህገ ወጥ መንገድ የወረሰ በመሆኑ የዋጋቸውን ግምት እና ያገኝ የነበረውን ጥቅም እንዲከፈለው የሚጠይቅ ሲሆን አመልካች በበኩሉ በጎችን መያዙን ሳይክድ ፍርድ ቤቱ ስልጣን የለውም፣ በሕገ ወጥ መንገድ ከሀገር ሲንቀሳቀሱ ተገኝተው የውርስ ውሳኔ የተሰጠባቸው መሆኑን በመግለጽ ተከራክሯል፡፡

እንደሚታወቀው የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 ምዕራፍ ሶስት ስር ከአንቀጽ 152 ጀምሮ ስለአቤቱታና ይግባኝ የተደነገገ ሲሆን በባለስልጣኑ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና በዋናው መሥሪያ ቤት ደረጃ የአቤቱታ አጣሪ የስራ ክፍል እንደሚቋቋም፤ ለአቤቱታ አጣሪው የሥራ ክፍል ቅሬታ ያስከተለው ውሳኔ በፅሁፍ በተሰጠ በ15 ቀናት ውስጥ አቤቱታ ሊቀርብ እንደሚችል፤ አቤቱታ አጣሪው የስራ ክፍልም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

በመመሪያ በሚወሰነው ጊዜ ውስጥ መርምሮ ውሳኔውን ለአቤቱታ አቅራቢው እንደሚያሳውቅ፤ በውሳኔው ላይ ቅር የተሰኘ ወገን ይግባኙን በገቢ ግብር አዋጅ መሰረት ለተቋቋመው የግብር ይግባኝ ጉባዔ ሊያቀርብ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡

በተመሳሳይ የፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 እንዲወጣ ከተፈለገባት ዓላማ አንዱ ታክስ ከፋዮች በታክስ ውሳኔ ረገድ የሚኖራቸውን ቅሬታ ማቅረብ የሚችሉበት ተደራሽነት ያለው፣ በሚገባ የተደራጀ እና የተቀላጠፈ ውሳኔ መስጠት የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ መገኘቱ ስለመሆኑ በአዋጁ መግቢያ (Preamble) ላይ ተመልክቷል፡፡ ይህን የአዋጁን አላማ ተግባራዊ ማድረግ ይረዳ ዘንድ የአዋጁ ክፍል ዘጠኝ የሚፈጠር አለመግባባት አቤቱታ የሚቀርብበትን ስርዓት ደንግጓል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ስር የሚገኘው አንቀጽ 52 እና ተከታይ ድንጋጌዎች በታክስ ህግ መሰረት ለባለስልጣኑ የቀረበ ማንኛውም ማመልከቻ ባለስልጣኑ ሳይቀበለው በሚቀርበት ጊዜ አለመቀበሉን የሚገልጸው ማስታወቂያ ማመልከቻውን ያልተቀበለበትን ምክንያቶች ያካተተ መሆን እንዳለበት፤ ታክስ ከፋዩ ቅሬታውን ማቅረብ የሚችልበት ስርዓት መዘርጋቱን፤ እንዲሁም ባለስልጣኑ በቅሬታው ላይ ውሳኔ ካልሰጠ አቤት ባዩ ይግባኙን ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ማቅረብ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 2(4) ስር በግልጽ እንደተመለከተው "ባለስልጣን" ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣንን፣ እንዲሁም የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ገቢዎች ቢሮን የሚመለከት ነው፡፡ ስለሆነም የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣንን ጨምሮ እነዚህ ባለስልጣኖች በሚሰጡት ውሳኔ ላይ ደግሞ ይግባኝ የሚቀርበው ደግሞ ከፍሲል እንደተገለፀው በአዋጁ ከአንቀጽ 52 ጀምሮ በተደነገጉት ድንጋጌዎች በተዘረጋው ሥርዓት መሰረት ነው፡፡ ስለሆነም አዋጅ ቁጥር 983/2008 የጉምሩክ ህግን ወይም ከጉምሩክ ጉዳዮች ጋር ተያይዘው የመጡ ክርክሮችን አይመለከትም የሚባልበት የህግ ምክንያት የለም፡፡

በተጨማሪም ከአስተዳደር ሥነ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 ግልጽ ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለው የአስተዳደር ተቋሙ የሰጠውን ውሳኔ ለአቤቱታ አቅራቢው በፅሁፍ መስጠት ያለበት መሆኑን፤ አቤቱታ አቅራቢውም በአስተዳደር ተቋሙ ውስጥ ያሉትን አስተዳደራዊ መፍትሔዎች ሁሉ አሟጦ ሊጨርስ እንደሚገባ፤ ይሁንና የአስተዳደር ተቋሙ አስተዳደራዊ መፍትሄ የመስጠቱን ሂደት ከሚገባው ጊዜ በላይ ያራዘመ እንደሆነ አስተዳደራዊ መፍትሄ አሟጦ መጨረስ ግዴታ እንደማይሆን ይደነግጋል፡፡

ከዚህም ሌላ ከጉምሩክ ስነ ስርዓት ጋር በተያያዘ ቅሬታ ያለው ሰው ቅሬታውን ለባለስልጣኑ አቤቱታ አጣሪ፤ ከዛም ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በየደረጃው ሳያቀርብ በቀጥታ ጉዳዩ በመደበኛ ፍርድ ቤት እንዲታይ የሚጠይቅበት የህግ አግባብ ስላለመኖሩ ይህ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 97372፣129430 እና በሌሎችም መዛግብት አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

ከፍሲል የተጠቀሱት የህጉ ድንጋጌዎች እንዲሁም የሰበር ውሳኔዎች ተያይዘው ሲታዩ በጉምሩክ ባለስልጣን የሚደረግ የንብረት መውረስን በመቃወም የሚቀርብ አቤቱታ ለዚሁ ተብሎ በተዘረጋው የህግ ስርዓት መሰረት ከሚስተናገድ በቀር በቀጥታ ለፍርድ ቤት ቀርቦ ውሳኔ ሊሰጥበት የሚችል አለመሆኑን ነው፡፡ ስለሆነም ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክርክር ያቀረባቸው በጎች በድሬዳዋ ከተማ ለመሸጥ ፈልጎ የበግ ዋጋ በመቀነሱ በደንባል ወረዳ ቢዮ ኩሉል ለማቆየት በመገደድ ለግጦሽ በተሰማሩበት በአመልካች ተወስደዋል በማለት የሚያቀርቡት ክርክር፤ እንዲሁም የስር ፍርድ ቤቶችም ይህን መከራከሪያ ተቀብለው በቀጥታ የቀረበውን ክስ በማስተናገድ ውሳኔ መስጠታቸው ከፍሲል የጠቀስነውን በህጉ የተዘረጋ ስርዓት የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች ያሳለፉት ብይንና ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚሁ መሰረት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**<u>ውሳኔ</u>**

1. የሱማሌ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 05-1-339/15 ሰኔ 29 ቀን 2015 ዓ.ም የሲቲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት የሰጠው ትእዛዝ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1//ሀ/መሰረት መሰረት ተሽሯል ፡፡
2. የሲቲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክሱን በቀጥታ ተቀብሎ ለመወሰን ስልጣን የለውም በማለት ወስነናል፡፡
3. አመልካችና ተጠሪ በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

**<u>መዝገቡ ተዘግቷል</u>**፡፡

<u>የ</u>ማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ. 253575

ህዳር 30 ቀን 2017 ዓ/ም

ዳኞች፡- ሽመክት አሰፋ

አለማየሁ ሹናሪ

ተናኜ ጥላሁን

ዋዚሞ ዋሴራ

ዘውዲቱ ታደሰ

አመልካች፡- አቶ ፍስሃ ወ/ገሪማ

ተጠሪ፡- 1/ የኢትዮጵያ ነዳጅ አቅራቢ ድርጅት

2/ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በዚሁ አግባብ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች በመስከረም 22 ቀን 2016 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌዴራል መጀመሪ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.303206 በጥር 18 ቀን 2015 ዓ/ም በዋለው ችሎ የሰጠው ብይን እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 305910 በሐምሌ 5 ቀን 2016 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡ ጉዳዩ የጉዳት ካሳን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር አመልካች ከሳሽ፣ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

አመልካች በሥር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ ንብረትነቱ የ1ኛ ተከሳሽ ተሽከርካሪ በሆነ ሹምዬ ከበደ በተባለ ሾፌር ሲሽከረከር በግንቦት 13 ቀን 2012 ዓ/ም ባደረሰብኝ ግጭት በቀኝ እጄ ጡንቻ አጥንት ላይ 20% ከፊል ቋሚ የአካል ጉዳት ስላደረሰብኝ፣ 2ኛው ተከሳሽ ለጉዳት አድራሹ ተሽከርካሪ የመድን ሽፋን የሰጠ በመሆኑና ከጉዳቱ በፊት በብሬይል በመታገዝ ሥራዎችን እሠራ የነበረ ሲሆን፣ ከጉዳቱ በኋላ የጽህፈት ሥራውን መሥራት ባለመቻሌ ገቢዬ ስለተቋረጠ፣ 2ኛ ተከሳሹ ብር 14,000 ከመክፈሉ በቀር ቀሪ የጉዳት ካሳ ለመክፈል ፈቃደኛ ስላልሆነ አደጋው በደረሰብኝ ጊዜ እድሜዬ 41 ዓመት ሲሆን፣ በቀሪ አማካኝ እድሜዬ 64.9 ድረስ 1/ ለ23.9 ዓመት የተቋረጠብኝ ገቢ፣ 2/ ወደ ህክምና ማዕከል እና ወደ ቤት ለመመላለስ ለትናስፖርት፣ 3/ ለአልሚ ምግብ ፣ 4/ ለአስታማሚ የወጣ ወጪ እና የሞራል ካሳ በአጠቃላይ ብር 654ፈ,403.18 ከ 9% ወለድ እና ከወጪ ኪሳራ ጋር ተከሳሾች በአንድነትና በነጣላ እንዲከፍሉኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የ1ኛ ተጠሪው መልስ በሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ ያልተመለከተ ሲሆን፣ 2ኛ ተጠሪ በሰጠው መልስ ለከሰሹ ብር 14,000 ከፍያቸው ጉዳዩ በእርቅ ያለቀ በመሆኑ ክሱ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በእርቅ ስምምነቱ ላይ ያሉ ምስክሮችን አስቀርቦ ከሰማ በኋላ 2ኛ 1ኛ ተከሳሽን ወክሎ የእርቅ ስምምነት ማድረግ አይችልም የሚለውን የከሳሽን ክርክር በተመለከተ 2ኛ ተከሳሽ ከ1ኛ ተከሳሽ ጋር ባለው የ3ኛ ወገን የመድን ውል መሠረት የተደረገ ስምምነት በመሆኑ የከሳሽን ክርክር ፍርድ ቤቱ አልተቀበለውም ካለ ሀኋላ ጉዳዩ በእርቅ ያለቀ ነው በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 244/2(መ) በሰጠው ብይን ክሱን ውድቅ አድርጎታል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም ይግባኝ ባይ የሆኑት የአሁን አመልካች ከአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ጋር የጉዳት ካሳ ስምምነት ማድረጋቸውን ባልካዱበት፣ የውሉንም ይዘት ጠንቅቀው የሚረዱ የህግ ባለሙያ በመሆናቸው የእርቅ ስምምነቱ አስረጂነት በህግ ተቀባይነት ያለው ነው የሚል ምክንያትን አስፍሮ የሥር ፍርድ ቤቱን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡

አመልካች በመስከረም 22 ቀን 2016 ዓ/ም በተጻፈ ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይህን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ሲሆን ይዘቱም የሥር ፍርድ ቤት ጉዳዩ በእርቅ ያለቀ ነው በማለት በብይን ክሱን ለመዝጋት መሠረት ያደረገው በ11/08/2013 ዓ/ም በአመልካችና 1ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገው ስምምነት ለአመልካች ተነቦላቸው ፈርመዋል በሚል በህግ ፊት የሚጸና የመጨረሻ የጉዳት ካሳ ክፍያ ስምምነት ተፈጽሟል በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ መሀይማንና ማየት የተሳናቸው ሰዎች የሚያደርጉት ውል በዳኛ ወይም በአዋዋይ ፊት መደረግ እንዳለበት በህግ ተደንግጎ እያለ ስምምነቱ በዚህ ሁኔታ መደረጉ ሳይረጋገጥ በውሉ ላይ ፈረሙ የተባሉት የ2ኛ ው ተጠሪ የራሱ ሠራተኞች በመሆናቸው ምስክርነታቸው እምነት የሚጣልበት ባለመሆኑና የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1730 በሚጠይቀው መሠረት ተስማሚ ወገኖች ፈቃዳችንን በመስጠት ስምምነቱን የፈጸምን መሆኑን የሚያሳይ ባለመሆኑና፣ የእርቅ ስምምነቱ ላይ 2ኛው ተጠሪ ያልፈረመ ከመሆኑም ሌላ በስምምነቱ

ላይ ፈቃዱን ያልሰጠው 1ኛው ተጠሪ ላይ ስምምነቱ ተፈጻሚ እንዲሆን በማድረግ የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ የግራ ቀኙ ጉዳይ በስምምነት አልቋል በማለት የተሰጠው ብይንና ተሽሮ የሥር ፍርድ ቤት በፍሬ ጉዳዩ ላይ አከራክሮ ውሳኔ እንዲሰጥ ይወሰንልን የሚል ነው፡፡

የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ አመልካቹ ከ2ኛው ተጠሪ ጋር በእርቅ ጨርሰዋል በማለት ክሱን በብይን ውድቅ የማድረጉን አግባብነትና 2ኛው ተጠሪ ከአመልካቹ ጋር አደረገው የተባለው የእርቅ ስምምነት 1ኛ ተጠሪ ላይ የሚኖረውን ውጤት በተመለከተ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንጻር ለመመርመር ሊመረመር የሚገባ ሆኖ በመገኘቱ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪ 1ኛ ተጠሪ በግንቦት 27 ቀን 2016 ዓ/ም የሰጠው መልስ ይዘት በአጭሩ አመልካች ምንም እንኳን ማየት የተሳናቸው ሰው ቢሆኑም በሙያቸው የህግ ባለሙያ ከመሆናቸውም በላይ በዚሁ ሙያ በመንግስጥ መ/ቤት ውስጥ የህግ ምክር አገልግሎት የሚሰጡ በመሆኑ በህጉ አግባብ ሊሟሉ የሚችሉ ጉዳዮችን በማናቸውም ሁኔታ ያልፋሉ ማለት አዳጋች ነው፡፡ ከ2ኛው ተጠሪ የካሳ ክፍያውን ሲቀበሉና ውሉንም ሲፈርሙ ገለልተኛ የሆነ የራሳቸውን ሰው ይዘው መጥተው ያመጡት ሰው ውሉን አንብቦላቸው ሙሉ ፈቃዳቸውን ሰጥተውና የውሉን ውጤት ተረድተው የፈረሙ በመሆኑ፤ መሐይማንና ማየት የተሳናቸው የውሉን ውጤት ሳይረዱ በሚገቡት ግዴታ ሊገደዱ እንደማይገባ የተደነገገውን ድንጋጌና የሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠውን ትርጉም ነው እንጂ ውጤቱን ተረድተው የተዋዋሉትን ውል እንዲያፈርሱ ባለመሆኑና የ1ኛ ተጠሪ ተሽከርካሪ ለሚያደርሰው ጉዳት 2ኛው ተጠሪ የጠቅላላ መድን ሽፋን የገዛ በመሆኑ 2ኛ ው ተጠሪ 1ኛውን ተጠሪ ተክቶ ሃላፊነቱን የሚወስድና የሚሸፍን በመሆኑ 1ኛ ተጠሪን ተክቶ በወቅቱ ተገቢውን ክፍያ ሲከፍላቸው አመልካች ሌላ የካሳ ክፍያ ሳይጠይቁ ተስማምተው የፈረሙ በመሆኑ 2ኛው ተጠሪ 1ኛ ተጠሪን ተክቶ ያደረገው የእርቅ ስምምነት እና ክፍያ 1ኛ ተጠሪን ከኃላፊነት ነጻ የሚያወጣ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቱ ብይን የሚነቀፍ አይደለም ተብሎ ከበቂ ኪሳራ ጋር በነጻ ልሰናበት ይገባል የሚል ነው፡፡

2ኛ ተጠሪ በግንቦት 28 ቀን 2016 ዓ/ም የሰጠው መልስ ይዘት በአጭሩ ከ1ኛው ተጠሪ ጋር ተመሳሳይ በሆነ መልኩ መልስ የሰጠ ሲሆን የሃላፊነት መጠንን በተመለከተ የ1ኛ ተጠሪ ተሽከርካሪ በሦስተኛ ወገኖች አካል እና ንብረት ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት እስከ ብር 40,000 የጉዳት ካሳ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ሲሆን የካሳ ስምምነት በማድረግ የህክምና ቦርድ ባቀረበው ሪፖርት መሠረት ብር 14,000 1ኛ ተጠሪን በመተካት ለአመልካች የከፈለ 2ኛ አመልካች ኃላፊነቱን በማያጠራጥር ሁኔታ የፈጸመ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ከበቂ ኪሳራ ጋር ያሰናብተን የሚል ነው፡፡

የአመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የግራቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር

አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ የቻልነው የአመልካቹ ቅሬታ መሠረት ያደረገው፣ አመልካቹን ማየት የተሳናቸው ከመሆናቸው አንጻር፣ ከ2ኛ ተጠሪው ጋር አደረጉት የተባለው የእርቅ ስምምነት በነጻ ፈቃዳቸው ያደረጉት ስምምነት ነው ሊባል የቻለው ተገቢው ማስረጃ ቀርቦ ስለመሆን አለመሆኑና የእርቅ ስምምነቱ ተደረገ የተባለው ክስ ከቀረበባቸው ውስጥ ከ2ኛው ተጠሪ ጋር ብቻ ሆኖ እያለ 1ኛ ው ተጠሪ ላይ የቀረበውን ክስ በተመለከተ 2ኛው ተከሳሽ 1ኛውን ተከሳሽ ወክሎ ያደረገው ስምምነት በመሆኑ አመልካቹ 2ኛው ተጠሪ 1ኛውን ተጠሪ ወክሎ የእርቅ ስምምነት ማድረግ አይችልም በሚል ያቀረቡት መከራከሪያ ተቀባይነት የሌለው ነው በማለት የሥር ፍርድ ቤት የደረሰበት ድምዳሜ ስህተት ነው በማለት ሲሆን፣ አመልካቹ ከ2ኛው ተጠሪ ጋር በሐምሌ 18 ቀን 2013 ዓ/ም አደረጉት የተባለው የእርቅ ስምምነት፣ ስምምነቱ በተደረገበት እለት ያልተፈረመ ስለመሆኑና በሚያዝያ ወር ላይ የተጻፈው ውል በሰኔ 1 ቀን 2013 ዓ/ም በመስክሮቹ የተፈረመ ስለመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት አስቀርቦ በሰማቸው ምስክሮች ማረጋገጡን በውሳኔው ላይ ካመለከተ በኋላ ምስክሮቹ በዚህ መልክ ያስረዱ ቢሆንም በተለምዶ የሚሠራበት ፎርም በመሆኑ የስምምነቱ ይዘት ውስጥ በመግባት ስምምነቱ ውድቅ የሚደረግበት አግባብ የለም ሲል የደረሰበትን ድምዳሜ ስንመለከት ማየት የተሳናቸው ወይም የመሐይማን ፊርማ የጣት ምልክት ፊርማ የነሱ ፊርማ መሆኑን ውል አዋዋይ ሹም ወይም አንድ ፍርድ ጸሐፊ  ወይም አንድ ዳኛ በሥራቸው ላይ ሆነው ያረጋገጧቸው ካልሆነ አያስገድዳቸውም በማለት የሚደነግግ ሆኖ እያለ ከዚህ የህግ ድንጋጌ የሚቃረን ምክንያት በመጥቀስ የእርቅ ስምምነት የተባለው ውል በተለምዶ የሚሠራበት ነው በማለት ህግን ሳይሆን ልማድን ለውሳኔው መሠረት በማድረግ ውሉን በመቀበል አመልካቹ የሚቃወሙትን ስምምነት አመልካቹን ተገዳጅ በሚያደርግ መልኩ የሥር ፍርድ ቤቱ ውሳኔ መስጠቱ እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም አመልካቹ የህግ ባለሙያ በመሆናቸው የውሉን ይዘት ጠንቅቀው የሚረዱ ናቸው በሚል ምክንያት ከላይ የተመለከተውን አመልካቹ ሊገደዱ የማይችሉበትን የህግ ድንጋጌ ከግምት ባለማስገባት አመልካቹ ተገዳጅ በማይሆኑበት የእርቅ ስምምነት ተገዳጅ ናቸው የሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ የሥር ፍርድ ቤቱን ውሳኔ ማጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ነው ብለናል፡፡

2ኛው ተጠሪ ከአመልካች ጋር አደረገ የተባለውን የእርቅ ስምምነት በተመለከተም የሥር ፍርድ ቤት የእርቅ ስምምነቱ የጉዳት አድራሹ ተሽከርካሪ ንብረት ለሆነው የ3ኛ ወገን የመድን ሽፋን የሰጠው 2ኛው ተጠሪ 1ኛውን ተጠሪ  በመወከል የእርቅ ስምምነት ማድረግ ይችላል የሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ፣ 1ኛ ተጠሪው ለክሱ መልስ እንዲሰጥ ስለመደረጉ ሳያረጋግጥና የ1ኛ ተጠሪን ክርክር በውሳኔው ላይ ሳያመለክት በመቅረት እንዲሁም አመልካቹ 1ኛ ተጠሪው፣ ከ2ኛው ተጠሪው ጋር በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ  እንዲባሉ በመጠየቅ ያቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄ ከ1ኛው ተጠሪ አንጻር ስለመቀበሉ ወይም ስላለመቀበሉ በውሳኔው ላይ ሳያሰፍር በመቅረት 1ኛውን ተጠሪን በተመለከተ በዝምታ ያለፈበትን አግባብም ስንመለከት ስለመድን ገቢው የኃላፊነት መጠን በተመለከተበት የተሽከርካሪ አደጋ የ3ኛ ወገን መድን አዋጅ ቁጥር 799/2005 በሦስተኛ ወገን የተሽከርካሪ አደጋ የመድን ፖሊሲው የካሳ መጠንን በሚመለከተው የአዋጁ አንቀጽ 16/2 ለህክምና

ማስ ታወሻ፡ - ይህ የ ሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነ ድ ለ ጥና ትና ምር ምር ሥራ ወይምለ ግን ዛ ቤ እ ን ጂ

ለ ፍር ድ አ ፈ ጻ ጸ ምዓ ላ ማአ ያ ገ ለ ግልም!

እና ሌሎች ከጉዳቱ ጋር ተያያዥነት ኖሯቸው አግባብ ባለው ህግ መሠረት ለሚከፈል ካሳ የተፈጸመ ወጪ ተጎጂው ቋሚ የአካል ጉዳት ወይም ሞት ሲደርስበት ከሚከፈለው የካሳ መጠን ላይ የሚታሰብ እንደሚሆን ሲደነግግ፣ የዚሁ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 3 ደግሞ በአዋጁ ንዑስ አንቀጽ 1 ከተወሰነው መጠን በላይ ካሳ ሊከፈለኝ ይገባል የሚል ሰው ይህንኑ ተጨማሪ ክፍያ መድን ገቢው ወይም በህግ ኃላፊነት የተጣለበት አካል እንዲከፍለው አግባብ ባለው ህግ መሠረት የመጠየቅ መብቱ የተጠበቀ ነው በማለት የሚደነግግ ሲሆን፣ አመልካቹ ሊከፈለኝ ይገባል በማለት የሚጠይቁት የካሳ ክፍያ 2ኛው ተጠሪ ከሰጠው የመድን ሽፋን የሚበልጥ ስለመሆን አለመሆኑና 2ኛ ተጠሪው በኋላፊነቱ መጠን አመልካችን ሊክስ የሚገባው የካሳ መጠን ፖሊሲውን መሠረት በማድረግ በሥር ፍርድ ቤቱ መጣራት የሚገባው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ጉዳት ላደረሰ ወገን የመድን ሽፋን የሰጠ አካል በሃላፊነቱ መጠን ለተጐጂው መካሱ ተጐጂው በጉዳት አድራሹ ላይ የሚያቀርበውን ተጨማሪ (ቀሪ) የካሣ ጥያቄ የሚከለክል ስላለመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 30536 ከሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም አንጻር፣ አመልካቹ ከ1ኛ ተጠሪው የሚጠይቁትን ቀሪ ካሳ በተመለከተ በህግ የተረጋገጠ የመጠየቅ መብታቸውን ባሳጣ መልኩ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይህን ስህተት ሳያርም በመቅረት የሥር ፍርድ በቤቱን ውሳኔ በማጽናት የሰጡት ውሳኔ የማስረጃ ምዘና መርህን የጣሰና መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል። በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል።

## ውሳኔ

1. የፌዴራል መጀመሪ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.303206 በጥር 18 ቀን 2015 ዓ/ም በዋለው ችሎ የሰጠው ብይን እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባን ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 305910 በሐምሌ 5 ቀን 2016 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ውሳኔው በሰበር ሥነሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1(ለ) መሠረት ተሽሯል ።
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መዝገቡን በማንቀሳቀስ አመልካች ከሁለቱም ተጠሪዎች የጠየቁትን ካሳ በተመለከተ የግራ ቀኙን ክርክርና መስረጃ በመመርመር ተገቢ የሆነውን ውሳኔ እንዲሰጥበት በሰበር ሥነሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/2 መሠረት ጉዳዩን ለሥር የፌ/መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መልሰናል።
3. ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻቻሉ።

## ትዕዛዝ

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፣ ይመለስ።

መ/ዐ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

የሰበር መዝገብ ቁጥር - 253719

ቀን - 27/03/2017 አ.ም

ዳኞች - ሽመክት አሰፋ

እንዳሻው አዳነ

አለማየሁ ሹናራ

ተናኜ ጥላሁን

ዋዚሞ ዋሲራ

አመልካች - የአፋር ክልል የኤትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የቀረበ የለም ከተባለ በኋላ ጠበቃ ጌታቸው ስለሺ ቀረቡ

ተጠሪዎች - 1. እንድሪስ ሰይድ

2. ኢትዮ ቴሌኮም } የቀረበ የለም

መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው ለምርመራ ስለሆነ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የተጀመረው በአፋር ክልል የአሩሲረሱ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት አመልካች 2ኛ ተከሳሽ ተጠሪ ከሳሽ አሁን የክርክሩ አካል ያልሆነው ኢትዮ ቴሌኮም 1ኛ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የስር ከሳሽ በስር ተከሳሾች ላይ ያቀረበው ክስ ይዘት ከሳሽ በአናጢነት ስራ የሚተዳደር መሆኑን ከስራው በቀን ብር 500.00 ገቢ የሚያገኝ መሆኑን ንብረትነቱ የ 1ኛ ተከሳሽ የሆነው ቢሮ ጣራ በብር 1,500.00 ለመስራት ከ 1ኛ ተከሳሽ ጋር ውል መግባቱን ስራውን በመስራት ላይ እያለ በጣራ ላይ በተዘረጋው የኤሌክትሪክ ገመድ በመያዙ ወደ መሬት በመውደቁ ከባድ የአካል ጉዳት የደረሰበት በመሆኑ ህክምና

ሲከታተል ቆይቶ የሀኪሞች ቦርድ 5% የአካል ጉዳት የደረሰበት መሆኑን በማረጋገጥ ማስረጃ የሰጠ በመሆኑ የከሳሽ እድሜ 35 አመት ስለሆነ ወደፊት 65 አመት ስለምኖር የ 30 አመት የአካል ጉዳት ምክንያት የተቋረጠብኝ ገቢ ካሳ ብር 270,000.00 ተከሳሾች በአንድነትና ነጠላ እንዲከፍሉ የሚል ነው፡፡ 1ኛ ተከሳሽ በሰጠው መልስ ተከሳሽ የመድን ሽፋን ያለው ስለሆነ ከሳሽ ክሱን በማሻሻል በመድን ላይ እንዲያቀርብ 1ኛ ተከሳሽ የህክምና ወጪ ለከሳሽ ከፍሏል፡፡ ያልከፈለው ህጋዊ ደረሰኝ ባለማቅረቡ ነው፡፡ ህጋዊ ደረሰኝ ቢያቀርብ ለመክፈል ፍቃደኛ ብንሆንም ከሳሽ ህጋዊ ደረሰኝ አላቀረበም የሚል መልስ አቅርቧል፡፡ ከ 2ኛ ተከሳሽ የአሁኑ አመልካች የቀረበ መልስ በአጭሩ ክርክሩ የስራ ውልን የሚመለከት ስለሆነ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም፡፡ ጉዳቱ የደረሰው በ 2ኛ ተከሳሽ ንብረት ምክንያት አይደለም፡፡ ጉዳቱ የደረሰው በ 2ኛ ተከሳሽ ንብረት ነው ቢባል እንኳን አደጋው የደረሰው በኤሌክትሪክ ስበት ምክንያት መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ከህክምና ተቋም የቀረበ የለም፡፡ ጉዳቱም የደረሰው በከሳሽ ጥፋትና ባለመጠንቀቁ ነው፡፡ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ መሰረት ኃላፊነት ሙሉ በሙሉ መውሰድ ያለበት 1ኛ ተከሳሽ ብቻ ስለሆነ 2ኛ ተከሳሽ ላይ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት የለውም ተብሎ እንዲወሰን የሚል ነው፡፡ የግራ ቀኙ የፅሁፍና የቃል ክርክር ከተጠናቀቀ በኃላ የከሳሽ የሰው ምስክሮች ቃል ተሰምቷል፡፡ የአመሰካከራቸው ሁኔታ በከሳሽ ላይ ጉዳት ሊደርስ የቻለው የተዘረጋ የመብራት ገመድ ምክንያት መሆኑን ከጣራ የወደቀው ቆጣሪ ሲጠፋ መሆኑን ከሳሽ ለህክምና ያወጣውን ወጪ በ 1ኛ ተከሳሽ ያልተከፈለ መሆኑን በጉዳቱ ምክንያት ከሳሽ በደሴ ሆስፒታል እንዲታከም ሪፈር ተደርጎ በኃላ ወደ አዲስ አበባ ሆስፒታል ሪፈር የተደረገ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ የግራ ቀኙ ክርክር ከተጠናቀቀ በኃላ ፍርድ ቤቱ መዝገቡን መርምሮ ከሳሽ የ 1ኛው ተከሳሽ ቤት ጣሪያ በመስራት ላይ እያለ በ 2ኛ ተከሳሽ ኤሌክትሪክ ገመድ ተይዞ በመሬት ላይ ወድቆ ጉዳት የደረሰበት በመሆኑ ከሳሽ የ 1ኛ ተከሳሽን ቤት እየሰራ ጉዳት የደረሰበት ቢሆንም ጉዳቱ የደረሰው የ 2ኛ ተከሳሽ ኤሌክትሪክ በመሆኑ ለጉዳቱ 2ኛ ተከሳሽ ኃላፊ ነው 1ኛ ተከሳሽ አላፊ አይደለም፡፡ የጉዳትን ካሳን በተመለከተ ከሳሽ ለህክምና ያወጣቸው ወጪዎች ብር 45,875.00 እና 5% የአካል ጉዳት የደረሰ በመሆኑ ጉዳት ካሳ 270,000.00 ብር 2ኛ ተከሳሽ ለብቻው እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡ የአሁን አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ቅሬታውን ለአፋር ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ ፍርድ ቤቱም መዝገቡን መርምሮ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔን አፅንቶታል፡፡

የአሁን ሰበር ቅሬታ የቀረበው ይህንን ውሳኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች ሰበር ቅሬታ በአጭሩ የፍ/ብ/ህ አንቀፅ 2069 ፍርድ ቤቱ በተሳሳተ መልኩ በመተርጎም አመልካችን አላፊ ማለቱ ስህተት ነው፡፡ አመልካች የዘረጋው የኤሌክትሪክ መስመር ሳይረግብና ፖሉ ሳይወድቅ ተጠሪ የ 1ኛ ተከሳሽ ቆርቆሮ ጣሪያ ላይ ወጥቶ በመያዙ ጉዳት የደረሰበት ስለሆነ አመልካች ኃላፊነት የለበትም፡፡ በከሳሽ ላይ የደረሰው ጉዳት በራሱ ቸልተኝነት ስለሆነ አመልካች አላፊ ነው የተባለው ፍርድ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ውድቅ እንዲሆን የሆስፒታል ማስረጃ በኤሌክትሪክ ምክንያት ጉዳት የደረሰ መሆኑን አይገልፅም፡፡ በስር ከሳሽ 1ኛ ተከሳሽ መካከል የስራ ግንኙነት ስላላቸው በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ መሰረት 1ኛ ተከሳሽ አላፊ

መሆን ሲገባው 1ኛ ተከሳሽን ከኃላፊነት ነፃ በመልቀቅ አመልካችን አላፊ ማለቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ እንዲሻርልኝ የሚል ነው፡፡

ይህ ችሎት አመልካች ላደረሰው ጉዳት ኃላፊ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ አግባብነትን ከፍ/ብ/ህ አንቀፅ 2069(1) አንፃር አጣርቶ ለመወሰን በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 28(3) መሰረት ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ የበኩሉን መልስ ያቀረበ ሲሆን ይዘቱ በአጭሩ ጉዳት የደረሰው የአመልካች ንብረት የሆነ የኤሌክትሪክ ምሶሶ ይዞኝ ወደ መሬት በመውደቁ ስለሆነ አመልካች ለደረሰብኝ ጉዳት አላፊ ነው መባሉ በአግባቡ ነው፡፡ በተጠሪ እና በስር 1ኛ ተከሳሽ መካከል በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ መሰረት እንዲዳኝ የሚያደርግ የስራ ግንኙነት የለንም፡፡ አመልካች የስር 1ኛ ተከሳሽ ተካቶ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ወደ ክርክር ውስጥ ገብቶ ካሳ ሊከፍል ይገባል በማለት ያቀረበው ቅሬታ አግባብ አይደለም፡፡ የካሳ መጠንን በተመለከተ አመልካች ክርክር ያላቀረበ ስለሆነ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ስለሆነ እንዲፀናልኝ የሚል ነው፡፡ አመልካች በ 16/07/2016 አ.ም በተፃፈ 04 ገፅ የመልስ መልሱን የሰበር ቅሬታውን በማጠናከር አቅርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ በተገለፀው መሰረት በመጠቃለሉ እኛም ለሰበር ቅሬታ መነሻ የሆነው ፍርድ፣ የግራ ቀኙን ክርክር ይህ ችሎት ካስቀረበው ጭብጥ አንፃር በተጠሪ ላይ ለደረሰው አካል ጉዳት አመልካች አላፊ ሊሆን የሚገባ መሆን አለመሆኑን አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር አገናዝበን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

መርምረን እንደተረዳነው ከሆነ 1ኛ ተጠሪ እንድሪስ ሰይድ በ 2ኛ ተጠሪ ቆርቆሮ ጣሪያ ላይ ወጥቶ በስራ ላይ እያለ የአመልካች ንብረት በሆነው በኤሌክትሪክ ገመድ ተይዞ መሬት ላይ ወድቆ ጉዳት መድረሱ አከራካሪ አይደለም፡፡ አመልካች የመብራት ሽቦ አልረገበም ወይም ፖሉ ወድቆ በመሬቱ ላይ አልተኛም 1ኛ ተጠሪ በራሱ ቸልተኝነት ጥንቃቄ ማድረግ ሲገባው የተጎዳው በመሆኑ አላፊ አይደለም አላፊነት ያለው በወቅቱ የቆርቆሮ ባለቤት የነበረው 2ኛ ተጠሪ ነው በማለት ይከራከራል፡፡ 1ኛ ተጠሪ የተጎዳው በአመልካች ንብረት በሆነው ኤሌክትሪክ ተይዞ እስከሆነ ድረስ በፍ/ብ/ህ አንቀ1ፅ 2069(1) መሰረት ከተጠያቂነት ሊያመልጥ አይችልም፡፡ አመልካች ከተጠያቂነት ነፃሊሆን የሚችለው ጥፋቱ የተጎጂው ሲሆን ብቻ እንደሆነ በፍ/ብ/ህ አንቀፅ 2086 ስር ተደንግጓል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ጥፋቱ የ 1ኛ ተጠሪ ስለመሆኑ አመልካች አላስረዳም፡፡ አመልካች የኤሌክትሪክ መስመር አልረገበም ፖሉም አልወደቀም 1ኛ ተጠሪ በቆርቆሮ ጣሪያ ላይ ወጥቶ ራሱ በእጁ ነክቶ ነው ጉዳት ያደረሰው ቢሉም የኤሌክትሪክ መስመር ሳይረግብ ወይም ፖሉ ሳይወድቅ በተዘረጋው መስመር እያለ ጉዳት ቢደርስ ከተጠያቂነት አያድንም፡፡ ከተጠያቂነት ነፃ ሊሆን የሚችለው የኤሌክትሪክ ሽቦ የአደጋ መከላከያ ፕላስቲክ የተሸፈነ መሆኑን ካስረዳ ነው፡፡ ከአመልካች በኩል የኤሌክትሪክ ሽቦን በአደጋ መከላከያ ፕላሽቲክ ተሸፍኗል የሚል ክርክር አልተነሳም፡፡

ሲጠቃለል በ 1ኛ ተጠሪ ላይ ጉዳት የደረሰው በአመልካች ንብረት በሆነው በኤሌክትሪክ ሽቦ ተይዞ መሆኑ የተረጋገጠ ስለሆነ 1ኛ ተጠሪ የ 2ኛ ተጠሪ ቤት እየሰራ ጉዳት ቢደርስበት ጉዳት አድራሹ የአመልካች ንብረት በመሆኑ 2ኛ ተጠሪ ከተጠያቂነት ነፃ በስር ፍርድ ቤት የተሰናበተው የሚነቀፍ አይደለም፡፡ በፍ/ብ/ህ አንቀፅ 2069(1) እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 57904 ቅፅ 11 ላይ በሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሰረት በ 1ኛ ተጠሪ ላይ ለደረሰው ጉዳት ሙሉ በሙሉ አመልካች አላፊ በመሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ባለመኖሩ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. አፋር ክልል የአሩሰረሱ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 10549 በቀን 07/09/2015 ኢ.ም የሰጠው ፍርድ እና የአፋር ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 5493 በቀን 22/12/2015 ኢ.ም የሰጠው ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የሌለ ስለሆነ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስነ ስርአት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9(1)(ሀ) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻቻሉ፡፡
4. በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠ እግድ ካለ ተነስቷል፡፡

## ትዕዛዝ

- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
## የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መዝገብ ቁጥር 253732

ህዳር 30 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች፡-----ሽመክት አሰፋ

አለማየሁ ሹናራ

ተናኜ ጥላሁን

ዋዚሞ ዋሲራ

ዘዉዲቱ ታደሰ

አመልካች፡-አቶ ታከለ በረዳ አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡-1ኛ/ ብሄራዊ የኢትዮጵያ ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ

2ኛ/ ኢስት ዌስት ኢትዮ ትራንስፖርት ኃ/የተ/ግ/ማ

3ኛ/ ቡና ኢንሹራንስ አ.ማ

(1ኛ–3ኛ) አልቀረቡም

4ኛ አዜብ አማረ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጠ

**ፍርድ**

ለፍርዱ መነሻ የሆነው ክርክር የመድን ሽፋን ዉልን መሰረት አድርጎ የመዳረግ መብትን መሰረት ያደረገ በፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የተጀመረ ሲሆን አመልካች ተከሳሽ፣ 1ኛ ተጠሪ ከሳሽ ሲሆኑ 2ኛ-4ኛ ተጠሪዎች ደግሞ ጣልቃ ገቦች ነበሩ፡፡1ኛ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ በአጭሩ፡- የአመልካች ንብረት የሆነዉ የሰሌዳ ቁጥሩ 3-36555 ኢት እና ተሳቢው 3-11999 ኢት መኪና በአፋር ክልል ውስጥ በመንዝ ላይ እያለ በተቃራኒ አቅጣጫ ሲጓዝ የነበረ የ2ኛ ተጠሪ መኪና በመግጨት እሳት እንዲነሳ በማድረግ 1ኛ ተጠሪ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

የመድን ሽፋን የሰጠው የደንበኞቻችን የሆኑት የሰሌዳ ቁጥር ኮድ-3-93835 ኢቲ ጎታች እና ተሳቢዉ የሰሌዳ ቁጥር 3-29007 ኢቲ የሆነዉን ተሽከርካሪ እንዲሁም የሰሌዳ ቁጥር 3-8976 ኢቲ የሆኑት ሁለት መኪኖች ሙሉ በሙሉ የወደሙ በመሆኑ 1ኛ ተጠሪ የከፈልኩትን ካሳ ብር 4,166,452.00/አራት ሚሊዮን አንድ መቶ ስልሳ ስድስት ሺህ አራት መቶ ሃምሳ ሁለት ብር/ ከወለዱ እና ወጪ እና ኪሳራ ጭምር አመልካች የመተካት ሃላፊነት አለበት የሚል ክስ አቅርቧል፡፡

አመልካች በበኩሉ የመጀመሪያ ደረጃ መቋወሚያ በማለት የ1ኛ ተጠሪ ክስ በፍትሀብሄር ሕጉም እና በንግድ ህጉ መሰረት ካሳ ለመጠየቅ ከተደነገገው የ2 ዓመት ይርጋ በኋላ የቀረበ በመሆኑ ክሱ በይርጋ

ይታገዳል ያለና በፍሬ ጉዳዩ ላይ የሰጡት መልስም ሲታይ ፦ለጉዳቱ መንስኤ የሆነውን መኪና በሽያጭ ለ4ኛ ተጠሪ ያስተላለፍኩ እና ሰነዶችንም ያስረከብኩ በመሆኑ ክሱ አይመለከተኝም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ 4ኛ ጣልቃ ገብም ከአመልካች ጋር ተመሳሳይ የሆነ የይርጋ መቋወሚያ አቅርቧል፡፡

በዚህ መልኩ ግራ ቀኙን በይርጋ መቋወሚያዉ ላይ ያከራከረዉ የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 1ኛ ተጠሪ በሰሌዳ ቁጥር 3-8976 ኢቲ ተሽከርካሪ ላይ የካሳ ክፍያ እንዲከፈል የ1ኛ ተጠሪ ቦርዱ የወሰነዉ በቀን 13/9/2011 ዓ.ም ሲሆን የካሳ ክፍያዉ የተከፈለዉ ሰኔ 4 ቀን 2011 ዓ.ም በመሆኑ 1ኛ ተጠሪ ደግሞ ክስ ያቀረበዉ ግንቦት 13 ቀን 2013 ዓ.ም ሲሆን ይህ ደግሞ የሁለት አመት ይርጋ ያላላፈበት በመሆኑ ከዚህ አንፃር የቀረበዉን የይርጋ በመቋወሚያ ዉድቅ በማድረግ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 3-93835 ኢቲ ጎታች እና በኮድ 3-29007 ኢቲ ተሳቢ ተሽከርካሪ ላይ የጉዳት ካሳ እንዲከፈል የ1ኛ ተጠሪ ቦርዱ የወሰነዉ በቀን 6/5/2011 ዓ.ም ሲሆን የመጀመሪያ ክፍያ በኮድ 3-93835 ኢቲ ጎታች ተሽከርካሪ ላይ የተከፈለዉ የካቲት 25 ቀን 2011 ዓ.ም ሲሆን 1ኛ ተጠሪ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 3-93835 ኢቲ ጎታች እና በኮድ 3-29007 ኢቲ ተሳቢ ተሽከርካሪ ላይ ያቀረበዉ የዳረጎት ክፍያ ክስ የተጠየቀዉ ግንቦት 13 ቀን 2013 ዓ.ም ስለሆነ ይህ ደግሞ 1ኛ ተጠሪ በእነዚህ ተሽርካሪዎች ላይ ያቀረበዉ ክስ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2143 (1) እና በንግድ ሕግ 674(1) መሰረት በሁለት አመት ይርጋ ጊዜ ካለፈዉ በኃላ በመሆኑ 1ኛ ተጠሪ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 3-93835 ኢቲ ጎታች እና በኮድ 3-29007 ኢቲ ተሳቢ ተሽከርካሪ ላይ ያቀረበዉ የዳረጎት ክፍያ ክስ በይርጋ የይታገዳል ሲል ብይን ሰጥቷል፡፡

1ኛ ተጠሪ በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝተዉ ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ ቅሬታ ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱ የጉዳት ካሳ ይርጋ መቆጠር የሚጀምረው የጉዳት ካሳው ተከፍሎ ከተጠናቀቀበት ጀምሮ እንጂ ጉዳት ከደረሰበት ጀምሮ እንዳልሆነ ሰ.መ.ቁ194880 ትርጉም የተሰጠበት በመሆኑ 1ኛ ተጠሪ ለኮድ 3-93835 መኪና ካሳ የከፈለው ግንቦት 12 ቀን 2011 ዓም ሲሆን ለተሳቢው ኮድ 3-29007 ደግሞ ካሳ የከፈለዉ መጋቢት 17 ቀን 2012 ዓ/ም በመሆኑ ይርጋው የሚቆጠረው 1ኛ ተጠሪ ለመጨረሻ ጊዜ ለአቶ መሀመድ ኑር ቀሪ የካሳ ክፍያ ብር 240 000.00/ሁለት መቶ አርባ ሺህ ብር/ ካሳ ከከፈለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ከመጋቢት 17 ቀን 2012 ዓ. ም ጊዜ ጀምሮ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው ሲል የስር የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠዉን ብይን በመሻር በኮድ 3-93835 ኢቲ እና በተሳቢው ኮድ 3-29007 ኢቲ ተሽከርካሪዎች ላይ የቀረበዉ ክስ በይርጋ አይታገድም ሲል ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም አመልካች የስር የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ እንዲታረም በማለት ሲሆን የቀረበው የሰበር አቤቱታውም የኮድ-3-93835 ኢቲ እና የኮድ 3-29007 ኢቲ ተሽከርካሪዎች በሚመለከት ክፍያ ከተከፈለበት 25/06/2011 ዓ/ም ጀምሮ ሁለት አመታት ጊዜ ውስጥ 1ኛ ተጠሪ በመዳረግ መብቱ ሳይጠቀም የቆየ ስለመሆኑ በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ሆኖ ሳለ 1ኛ ተጠሪ በእነዚህ ተሽከርካሪዎች ላይ ያቀረበው ክስ በይርጋ የሚዘጋ ሆኖ እያለ 1ኛ ተጠሪ ለተለያዩ ደንበኞች የከፈለውን የተለያየ ካሳ በሚመለከት በተለያዩ ደንበኞች እግር ተተክቶ መብቱን የሚጠይቅ እንደመሆኑ መጠን ይርጋ ያላላፈን

የሌሎች ደንበኞቹን ጉዳይ አጣምሮ ስለከሰሰ ብቻ በተጠቀሱት መኪኖች ላይ የቀረበው ክስ በይርጋ አልታገደም ሊባል አይችልም፡፡የመጨረሻ ጊዜ ክፍያ የሚያገለግለው መጨረሻ ለተከፈለለት ደንበኛ ብቻ እንጂ የይርጋ ጊዜ ላለፈበት ደንበኛ ለተከፈለ ክፍያ አይደለም ስለሆነም በተጠቃሾቹ መኪኖች ላይ ክፍያ ከተፈጸመ ጀምሮ ይርጋ ያለፈበት ክስ ስለመሆኑ በስር ፍ/ቤት ተረጋግጦ እያለ የስር የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ለተለያዩ ደንበኞች እና መኪኖች የተከፈለ ካሳን መሰረት አድረጎ የቀረበን ክስ አግባብነት የሌለውን የሰ.መ.ቁ 194880 በመጥቀስ የሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲታረምልን የሚል ነው፡፡

አመልካች ያቀረቡትን የሰበር ቅሬታ መነሻ ተደርጎ የሰ.ቁ 3-93335 የሆነው ጎታች መኪና እና የሰ.ቁ 3-29007 የሆነ ተሳቢ መኪና ባለቤት የተለያዩ ሰዎች ከመሆናቸው አኳያ በሁለቱም መኪኖች የመድን ሽፋን የተሰጠው በአንድ የመድን ውል መሆኑን እንዲሁም የጎታቹ እና በተሳቢው ላይ ጉዳት የደረሰው በአንድ የአደጋ ክስተት መሆኑን ጠቅሶ የይርጋ ጊዜው አላለፈም የሚል የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ግራ ቀኙ በተገኙበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት ተጠሪዎች መልሳቸውን እንዲያቀርቡ አዟል ፡፡

1ኛ ተጠሪ ባቀረቡት መልስም አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ፡- የሰ.ቁ 3-93835 ኢቲ እና 3-29007 ኢት የተሳቢው አንድ አካል የሆነ እና በአንድ የመድን ውል የመድን ሽፋን ተሰጥቶት እያለ ይህም መኪኖቹን እንደ አንድ የመኪና አካል የሚያስቆጥር በመሆኑ አንድ የካሳ ማደህር ተከፍቶ ካሳ ተከፍሎላቸው እያለ አመልካች የተለያዩ መኪናዎች አድርጎ ይርጋው በተለያየ ጊዜ ጀምሮ እንዲቆጠር ያቀረበው አቤቱታ ስህተት ነው፡፡የመድን ውል የገባውም የተለያዩ ሰው ሳይሆን የጎታቹ መኪና ባለንብረት ለተሳቢውን ውል የያዘ ሲሆን በመድን ገቢው ፍቃድ ካሳው ስመ ሀብቱ ተመዝግቦ ስለሚገኝ ሰው የተሰጠ በመሆኑ ለተለያዩ ደንበኛ እንደተከፈለ ካሳ መቆጠር የለበትም፡፡የሰ/መ/ቁ 194880 የካሳ ጊዜው መቆጠር የሚጀምረው አደጋው ከደረሰ ጊዜ ጀምሮ ሳይሆን ካሳ ተከፍሎ ከተጠናቀቀበት ነው በማለት ከሰጠው የህግ ትርጉም አንጻር በአንድ የመድን ውል መሰረት በተሰጠ የመድን ሽፋን ንብረት ላይ ጉዳት በደረሰ ጊዜ የካሳ አከፋፈል አሰራሩ በአንድ የካሳ ማህደር በመሆኑ የይርጋ ጊዜው መቆጠር ያለበት ካሳውን ሙሉ በሙሉ ከፍሎ ካጠናቀቀበት ጊዜ ጀምሮ ስለመሆኑ የሚገልጽ በመሆኑ በስር ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ ተጠቃሹን የሰበር ትርጉም ያገናዘበ በመሆኑ ሊጸና ይገባል ሲሉ መልስ ሰጥቷል፡፡

ከ2ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ባቀረቡት መልስም 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ለደንበኞቹ ካሳ ከከፈለበት ጊዜ አንስቶ በ2 ዓመት ጊዜ ውስጥ የመዳረግ መብቱን በመጠቀም ክስ ያላቀረበበት ስለመሆኑ በስር ፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መወሰኑ አግባቡ መሆኑን ጠቅሰው የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ ስህተት ነው ሊታረም ይገባል ሲሉ የአመልካችን አቤቱታ ደግፈው መልስ ሰጥቷል፡፡

3ኛ ተጠሪ በበኩሉ ኢንሹራንስ ተቋሙ ለእያንዳንዱ ደንበኛ ክፍያ ከፈጸመበት ጊዜ ጀምሮ ይርጋ ይቆጠር ቢባል ጉዳዮች በተቻለ መጠን በአንዴ ተጠቃለው መቅረብ አለባቸው የሚለውን የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 216 የሚጻረር እና በፍ/ቤቶች ላይ ተያያዥ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የተለያየ ክስ እያቀረበ የስራ መጨናነቅን የሚያስከትል በመሆኑ የቀረበው አቤቱታ ተገቢ አይደለም በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ይጽናልን ሲሉ መልስ ሰጥቷል፡፡

አጠር አጠር ባለ መልኩ የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ የተጠቀሰዉን የሚመስል ሲሆን ይህ ፍርድ ቤትም ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንፃር መዝገቡን እንደመረመርነዉም አመልካች እያቀረበ ያለዉ ክርክር በሰሌዳ ቁጥር 3-93835 ኢቲ ጎታች ተሽከርካሪ እና ኮድ 3-29007 ኢቲ ተሽከርካሪ ላይ ለደረሰባቸዉ እሳት ቃጠሎ ጉዳቱ በቦርድ እንዲወሰን ተደርጎ ካሳ ከከፈለ ከሁለት አመት በኃላ 1ኛ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ያቀረበዉ ክስ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2143(1) እና በንግድ ሕግ ቁጥር 674(1) መሰረት በሁለት አመት በይርጋ ቀሪ ሊሆን ሲገባዉ 1ኛ ተጠሪ ለተለያዩ ተሽከርካሪዎች ለተለያዩ ደንበኞቹ በተለያየ ጊዜያት ክፍያ የከፈላባቸዉና የሁለት አመት ይርጋ ጊዜ ያለፈባቸዉን በመሉ 1ኛ ተጠሪ የመጨረሻዉን ክፍያ ለተሳቢ መኪናዉ ባለቤት ለሆነዉ ለአቶ መሃመድ ኑር የከፈለዉ ከመጋቢት 17 ቀን 2012 ዓ.ም ስለሆነ ክስ የቀረበዉ ግንቦት 13 ቀን 2013 ዓ.ም በመሆኑ ክሱ ሲቀርብ ሁለት አመት ያላለፈዉ በመሆኑ ይህን በተመለከተ የቀረበዉ ክስ በይርጋ አይታገድም መባሉ ተገቢነት የሌለዉ ነዉ ሲሉ የተከራከሩ ሲሆን አመልካችን ክርክር በሚደግፍ መልኩ 3ኛ ተጠሪ ደግሞ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሊሆን አይገባም መባሉ ተገቢት የሌለዉ ነዉ ሲሉ የበኩላቸዉን ክርክር አቅርቧል፡፡1ኛ ተጠሪ በበኩሉ በሰሌዳ ቁጥር 3-93835 ኢቲ ጎታች ተሽከርካሪ እና ኮድ 3-29007 ኢቲ ተሳቢ የሆኑት ተሽርካሪዎች የመድን ዋስትና በአንድ መድን ዉል ጎታች እና ተሳቢዉ ላይ ያለዉን የመድን ሽፋን ፖሊሲ የሆነዉን ክፍያ አጠቃሎ የመጨረሻዉን ክፍያ ከከፈለ በኃላ ያለዉ ጊዜ ታይቶ የይርጋ ጊዜ አላለፈዉም መባሉ በአግባቡ ስለሆነ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ተገቢነት ያለዉ ነዉ የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡

በዚህ ጉዳይ የሰሌዳ ቁጥር 3-93835 ኢቲ ጎታች ተሽከርካሪ እና ኮድ 3-29007 ኢቲ ተሳቢ ተሽከርካሪ የተለያዩ ደንበኞች ባለንብረት የሆኑበትና በአንድ የመድን ዉል ፖሊሲ ዋስትና የሰጠበት ሲሆን የእነዚህ ጎታችና ተሳቢዉ የመኪና ባለቤት የተለያዩ ደንበኞች በመሆናቸዉ ጋር በተያያዘ በተሽከርካሪዉ ላይ የእሳት ቃጠሎ ጉዳት በመድረሱ ለተሽከርካሪዎቹ የተከፈለዉን የመድን ሽፋን ለመኪኖቹ ባለቤት የተለያየ ጊዜ በመድን ዉሉ መሰረት ይህም ለሰሌዳ ቁጥር 3-93835 ኢቲ ጎታች ተሽከርካሪ ባለቤት 1ኛ ተጠሪ የካሳ ክፍያዉን አጠቃሎ የከፈለዉ ግንቦት 12 /2011 ዓ.ም ሲሆን ለኮድ 3-29007 ኢቲ ባለቤት ለሆነዉ ተሳቢ 1ኛ ተጠሪ የመጨረሻ ክፍያ የከፈለዉ መጋቢት 17 ቀን 2012 ዓ.ም ነዉ 1ኛ ተጠሪ ክሱን ለፍርድ ቤት ያቀረበዉ ደግሞ ግንቦት 13 ቀን 2013 ዓ.ም ስለመሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ በእጃችን ባለዉ ጉዳይ የስር ፍርድ ቤት ሁለት የተለያዩ ንብረቶች የተለያየ ባለቤትነት የሆኑትን ከላይ የተጠቀሱትን ተሽከርካሪዎች በአንድ የመድን ዋስትና የገቡ ስለሆነ ለሰሌዳ ቁጥር 3-93835 ኢቲ ጎታች ተሽከርካሪ ባለቤት ተጠቃሎ የመጨረሻ ካሳ በ1ኛ ተጠሪ የተከፈለዉ በግንቦት 12 ቀን 2011 ዓ.ም ሲሆን ይህ ደግሞ 1ኛ ተጠሪ የመዳረግ መብቱን መሰረት አድርጎ ክሱን ግንቦት 13 ቀን 2013 ዓ.ም ሲያቀርብ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2143(1) እና በንግድ ሕግ ቁጥር 674(1) መሰረት በሁለት አመት የይርጋ ጊዜ ያለፈዉ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ኮድ 3-29007 ኢቲ ለሆነዉ ተሳቢ ተሽከርካሪ 1ኛ ተጠሪ የመጨረሻ ክፍያ ለንብረቱ ባለቤት

ለሆነዉ ለአቶ መሀመድ ኑር የከፈለዉ መጋቢት 17 ቀን 2012 ዓ.ም ሲሆን ይህ ለኮድ 3-29007 ኢቲ ለሆነዉ ተሳቢ ተሽከርካሪ ላይ ክፊያ ከተከፈለበት ጊዜ አንስቶ 1ኛ ተጠሪ ክስ እስካቀረበበት ጊዜ ያለዉ ይህም ግንቦት 13 ቀን 2013 ዓ.ም ድረስ ሲታይ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2143(1) እና በንግድ ሕግ ቁጥር 674(1) መሰረት በሁለት አመት ይርጋ ጊዜ ያላለፈበት መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ የስር የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሰሌዳ ቁጥር 3-93835 ኢቲ ጎታች ተሽከርካሪ እና ኮድ 3-29007 ኢቲ ተሳቢ የሆኑት ተሽርካሪዎች የመድን ዋስትናዉ የተሰጠዉ ለጎታቹ እና ለተሳቢዉ በመሆኑ የመጨረሻዉ ክፍያ ለአቶ መሀመድ ኑር የተከፈለዉ መጋቢት 17 ቀን 2012 ዓ.ም ስለሆነ ይህ ደግሞ የመጨረሻ ክፍያ ተደርጎ የሚመቆጠር በመሆኑ በሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 194880 በተሰጠዉ አስገዳጅ ትርጉም መሰረት 1ኛ ተጠሪ ክሱን ሲያቀርብ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2143(1) እና በንግድ ሕግ ቁጥር 674(1) መሰረት የሁለት አመት ይርጋ አላለፈዉም ሲል የደረሰበትን መደምደሚያ አግባብነት እንደሚከተለዉ የመርምረናል፡፡

የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 194880 ላይ ይርጋዉን ጊዜ የሚታሰበዉ መድን ሰጪዉ ካሳዉን ከከፈለበት ቀን አንስቶ እንደሆነ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሰጠበት ሲሆን በዚህ አስገዳጅ ዉሳኔ ላይ የመድን ዉል የተገባባት ባለንብረት ሆነ ንብረቱ የአንድ ሰዉ ሲሆን አሁን በአኛችን ባለዉ ጉዳይ የተለያዩ ባለ ንብረቶች በተለያየ ንብረት ላይ በአንድ የመድን ዋስትና የገቡ ሲሆን መድን ክፍያዉም በተለያየ ጊዜ ለተለያዩ ንብረቶች ለተለያየ ደንበኞች የተከፈለ ሲሆን ይህም 1ኛ ተጠሪ ለሰሌዳ ቁጥር 3-93835 ኢቲ ጎታች ተሽከርካሪ ባለቤት የመጨረሻዉ የካሳ ክፍያ የከፈለዉ ግንቦት 12 ቀን 2011 ዓ.ም ሲሆን 1ኛ ተጠሪ የከፈለዉን ካሳ መሰረት አድርጎ ያቀረበዉ የዳረጎት ክስ ደግሞ ግንቦት 13/2013 ዓ.ም ሲሆን ይህ ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2143(1) እና በንግድ ሕግ ቁጥር 674(1) መሰረት ሁለት አመት የይርጋ ጊዜ ያለፈበት ስለመሆኑ አከራካሪ አይደለም ሌላዉ ለኮድ 3-29007 ኢቲ ተሳቢ ላይ 1ኛ ተጠሪ የመጨረሻዉ ክፍያ ለንብረቱ ባለቤት ለአቶ መሀመድ የተከፈለዉ መጋቢት 17 ቀን 2012 ዓ.ም ሲሆን ይህ ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2143(1) እና በንግድ ሕግ ቁጥር 674(1) መሰረት የሁለት አመት የይርጋ ጊዜ ያላላፈበት ስለመሆኑ ግልፅ ነዉ በመሆኑም የስር የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰሌዳ ቁጥር 3-93835 ኢቲ ጎታች ተሽከርካሪ ባለቤት የመጨረሻ ክፍያ ከተከፈለዉ የይርጋ ጊዜ ያለፈበትን ደንበኛ የሁለት አመት ይርጋ ያላለፈዉን የመጨረሻ ክፍያ የተከፈለዉን የኮድ 3-29007 ኢቲ ተሳቢ የንብረት ባለቤት ጋር በመቀላቀል በሰሌዳ ቁጥር 3-93835 ኢቲ ተሽከርካሪ ላይ የተጠየቀዉን የዳረጎት ክፍያ ጥያቄ በይርጋ አይታገድም ሲል የደረሰበት መደምደሚያ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ዉሳኔ

1/ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 243367 ላይ በሐምሌ 28 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ በማሻሻል የሰጠዉ ዉሳኔ በፌ/ጠ/ፍ/ቤት የሰበር ስነ ስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1)(ለ) መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2/ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 243367 ላይ በሐምሌ 28 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት በሰሌዳ ቁጥር 3-93835 ኢቲ ጎታች ተሽከርካሪ ላይ በ1ኛ ተጠሪ የተጠየቀዉ የዳረጎት ክፍያ ጥያቄ ይርጋ ጊዜዉ አላለፈም ሲል የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ በመሻር የሰጠዉ ዉሳኔ ክፍል አግባብነት የሌለዉ በመሆኑ በፌ/ጠ/ፍ/ቤት የሰበር ስነ ስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1)(ለ) መሰረት ተሽሯል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ዉሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

3/ የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 272916 ላይ ጥር 2 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት በሰሌዳ ቁጥር 3-93835 ኢቲ ጎታች ተሽከርካሪ ላይ በ1ኛ ተጠሪ የተጠየቀዉ የዳረጎት ክፍያ ጥያቄ በይርጋ ይታገዳል ሲል የሰጠዉ ዉሳኔ ክፍል በአግባቡ ስለሆነ በፌ/ጠ/ፍ/ቤት የሰበር ስነ ስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1)(ሀ) መሰረት ፀንቷል፡፡

4/ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 243367 ላይ በሐምሌ 28 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት በሰሌዳ ቁጥር 3-29007 ኢቲ ተሳቢ በሆነ መኪና ላይ በ1ኛ ተጠሪ የተጠየቀዉ የዳረጎት ክፍያ በይርጋ አይታገድም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ በመሻር ጉዳዩን ተቀብሎ እንዲያስተናገድ ወደ ስር ፍርድ ቤት በመመለስ የተሰጠዉ የዉሳኔ ክፍል በአግባቡ በመሆኑ በፌ/ጠ/ፍ/ቤት የሰበር ስነ ስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1)(ሀ) መሰረት ፀንቷል፡፡

2/ ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ወገኖች ይቻቻሉ፡፡

በዚህ መዝገብ የተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ ካለ እንዲነሳ ቷዟል ፡፡ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

የሰ/መ/ቁ 254045

ህዳር 26 ቀን 2016 ዓ/ም

ዳኞች ፡-ሽመክት አሰፋ

አለማየሁ ሹናራ

ዋዚሞ ዋሴራ

ተናኜ ጥላሁን

ዘውዲቱ ታደሰ

አመልካች፡- ሐረማያ ዩኒቨርስቲ አልቀረቡም

ተጠሪ፡- አልይ አብዱራህማን አልቀረቡም

መዝገቡ ለምርመራ ሲሆን ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች በጥቅምት 7 ቀን 2016 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ፣ የሐረሪ ህ/ክ/መ/ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 24684 በሐምሌ 28 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ፣ እንዲሁም የሐረሪ ህ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 07051 በመስከረም 28 ቀን 2016 ዓ.ን በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

ጉዳዩ የጉዳት ካሳን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በሐረሪ ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር አመልካች 1ኛ ተከሳሽ፣ ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ በዚህ የሰበር ክርክር ተካፋይ ያልሆኑ አቶ ሰለሃዲን መሀመድ 2ኛ ተከሳሽ፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ጣልቃ ገብ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ የ1ኛ ንብረት የሆነውን ተሽከርካሪ 2ኛው ተከሳሽ ሲያሽከረክር የከሳሽ ንብረት የሆነውን ባጃጅ ተሽከርካሪ በመግጨት ጉዳት ያደረሰ ስለሆነ የተቋረጠ ገቢ

እንዲከፍለኝ እና ባጃጁ 10 ዓመት ሙሉ እንዳይንቀሳቀስ በማድረጉ የባጃጁ ሞተር አፈር እንዲሆንና እንዲዝግ ያደረገ በመሆኑ አዲስ ባጃጅ እንዲተካልኝ ወይም የባጃጁን ዋጋ እንዲከፍለኝ በማለት በድምሩ ብር 1,280,000/አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሰማንያ ሺ/ በአንድነትና በነጠላ ተከሳሾቹ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የሥር 1ኛ ተከሳሽ የሆነው አመልካች በሰጠው መልስ ጉዳት አድራሹ የ1ኛ ተከሳሽ ተሽከርካሪ የጣልቃ ገቡ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ሽፋን ስላለው ኃላፊነቱ የመድን ድርጅቱ ነው፡፡ የተቋረጠ ገቢ የተባለውን በተመለከተ የተጋነነ ስለሆነና በግብር ሰብሳቢ ወይም በትራንስፖርት መ/ቤት ያልተገመተ ስለሆነ ግምቱ ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ ከዚህም ሌላ ከሳሽ የንብረቱን ጠቅላላ ዋጋ ግምት እየጠየቀ በሌላ በኩል ደግሞ አዲስ ባጃድ ለመተካት መጠየቁ ተገቢነት የሌለው ነው፡፡ መድን ድርጅቱ ጣልቃ ይግባልኝ እና እኔ በነጻ እንድሰናበት በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የሥር ፍርድ ቤት ወደ ክርክሩ እንዲገባ ያደረገው የኢትዮጵያ መድን ድርጅት በሰጠው መልስ የጉዳት አድራሹ ተሽከርካሪ ሾፌር ተገቢውን መንጃ ፈቃድ ያልያዘ ስለነበረ ከ1ኛ ተከሳሽ ጋር በገባው ውል መሠረት ጣልቃ ገብ ኃላፊነት የለበትም፡፡ ጣልቃ ገብ ተጠያቂ ነው ቢባል እንኳ በአንድ የአደጋ ክስተት እስከ ብር 100,000/አንድ መቶ ሺ/ብቻ ለመክፈል የምንገደድ ሲሆን፣ በዚያው አደጋ ከከሳሹ ባጃጅ ሌላ፣ የአቶ ማህቡብ ኡመርን በሬ የ1ኛ ው ተከሳሽ ተሽከርካሪ ገጭቶ ጉዳት በማድረሱ ጣልቃ ገብ ለበሬው ባለቤት ብር 67,000/ስድሳ ሰባት ሺ/ የከፈለ በመሆኑ ጣልቃ ገብ ሃላፊነት አለበት ከተባለ እንኳ ቀሪውን ብር 32,500/ሰላሳ ሁለት ሺ አምስት መቶ/ ብቻ ለኪከፍል ይገባል ይባልልን በማለት ተከራክሯል፡፡

የሥር ፍርድ ቤቱ ካሳ የመክፈል ኃላፊነቱ የማን ነው? የሚልና ተያያዥ ጭብጦችን ከያዘ በኋላ የቀረቡትን ማስረጃዎች መርምሮ ኃላፊነቱ የ1ኛ ተከሳሽ እና የጣልቃ ገብ ነው ካለ በኋላ በጊዜ ባለመጠገኑ የወደመውን የከሳሽን ባጃጅ 1ኛ ተከሳሽ በአዲስ እንዲተካ ወይም የባጃጁን ግምት በገበያ ዋጋ መሠረት ለከሳሽ ይክፈል ቅሪተ አካሉን ይውሰድ በማለት ወስኖ፣ ተጠሪው ያቀረቡትን የታጣ ገቢ ጥያቄ ውድቅ አድርጎታል፡፡ የጣልቃ ገቡ ኃላፊነት ብር 32,500/ሰላሳ ሁለት ሺ አምስት መቶ/ነው፣ 2ኛ የሥር ተከሳሹን በተመለከተ ጉዳዩ በሌለበት የታየ ሲሆን የሥር ፍርድ ቤቱ 2ኛ ተከሳሽን አስመልክቶ ተጠሪው ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄን በዝምታ ነው ያለፈው፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለይግባኝ ሰሚው የሐረሪ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም ውሳኔው ሳይለወጥ ቀርቷል፡፡

አመልካች በጥቅምት 2 ቀን 2016 ቀን ጽፎ ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ይህን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ሲሆን ይዘቱም የሥር ፍርድ ቤት አግባብ ባለው ማስረጃ ሳያጣራ ባጃጁ ላይ የደረሰው ጉዳት በጊዜው ጥገና ስላላገኘ ወደ ጠቅላላ ጉዳት ተቀይሯል በማለት መወሰኑ፣ እንዲሁም የአሁን ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ቀረቡ ክስ የዳኝነት ጥያቄያቸው 1ኛ ተከሳሽ የሆነውን አመልካችን እና የአመልካች ተሽከራካሪ ሾፌር የሆነው አቶ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ሳላሐዲን መሐመድን  በአንድነት እና በነጠላ ኃላፊነት ተጠያቂ እንዲሆኑ በማለት ሲሆን፣ የሥር ፍርድ ቤቱ 2ኛ ተከሳሽን ተጠያቂነት አስመልክቶ ሳይወስን በአመልካች ላይ ብቻ መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነና ይግባኝ ሰሚው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ይህን ስህተት ማረም ሲገባው የአመልካችን ይግባኝ ውድቅ ማድረጉ መሠረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ ውሳኔው እንዲሻርና በነጻ እንድንሰናበት ይወሰንል የሚል ነው፡፡

የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ባጃጁ ላይ በደረሰው ጉዳት በጊዜው ተገቢውን ጥገና ስላላገኘ ወደ ጠቅላላ ጉዳት ተቀይሯል በማለት የሥር ፍርድ ቤቱ  የደረሰበት ድምዳሜ እና የካሳን መጠን በተመለከተ ጉዳቱ በደረሰበት ጊዜና መጠን ሳይሆን፤ በኋላ ተከስቷል ባለው ጉዳት መጠን የወሰነበት አግባብ  እንዲሁም የ2ኛ የሥር ተከሳሽ ሃላፊነትን በመለከተ ከተጠየቀው ዳኝነት አንጻር ሊመረመር ይገባል በሚል ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት መጥሪያ ተልኮላቸዋል፡፡

ተጠሪ  መጥሪያ ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆናቸው በመረጋገጡ መልስ የመስጠት መብታቸውን በማለፍ በህዳር 19 ቀን 2016 ዓ/ም በዋለው ችሎት ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡

የግራቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፣ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ የቻልነው የሐረሪ ህ/ክ/መ/ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባጃጁ ላይ በደረሰው ጉዳት በጊዜው ተገቢውን ጥገና ስላላገኘ ወደ ጠቅላላ ጉዳት ተቀይሯል በማለት የደረሰበት ድምዳሜን በተመለከተ ጉዳት የደረሰበትን ባጃጅ 1ኛ የሥር ተከሳሽ የሆነው የአሁን አመልካች ሳያስጠግን በመቅረቱ የባጃጁ ጉዳት ጠቅላላ ጉዳት/total loss/ እንደደረሰ የሥር ከሳሽ የሆኑት ተጠሪው እንዳስረዱ በውሳኔው የገለጸ በመሆኑ ፍሬ ጉዳዩን በማስረጃ የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው የሥር ፍርድ ቤት የባጃጁን ጉዳት ጠቅላላ ጉዳት መሆኑን በማስረጃ በማረጋገጡ ድምዳሜው የሚነቀፍ አይደለም፡፡

የካሳውን መጠን በተመለከተም አዲስ ባጃጅ አመልካቹ ለተጠሪው እንዲተካ ወይም የባጃጁን ግምት በገበያ ዋጋ እንዲከፍል በማለት ሲወስን ከዚሁ ጋር በማያያዝ ጉዳት የደረሰበትን ባጃጅ ቅሪተ አካል አመልካች እንዲወስድ በማለት የወሰነ ከመሆኑ አንጻር አመልካቹ ለተጠሪው አዲስ ባጃጅ የሚተካላቸው ቢሆን ወይም የገበያውን ዋጋ ለተጠሪ የሚከፍል ቢሆን ቅሪተ አካሉን አመልካቹ የሚወስድ ከመሆኑ አንጻር  የቅሪተ አካሉ ዋጋ ለአመልካቹ አዲሱን ባጃጅ ከገዛበት ወይም ከባጃጁ የገበያ ዋጋ ላይ ተቀናሽ  ሲደረግ የአመልካቹ ሃላፊነት ከአዲሱ ባጃጅ ዋጋ የቀነሰ እንደሚሆን መረዳት የሚቻል በመሆኑ በዚህ ረገድ የሥር ፍርድ ቤቱ የሰጠው ውሳኔም የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

የ2ኛ የሥር ተከሳሽ ሃላፊነትን በተመለከተ ዳኝነት የጠየቁት የአሁን ተጠሪ በመሆናቸው፣ በ2ኛው ተጠሪ ላይ ስለቀረበው ክስ የሥር ፍርድ ቤት በዝምታ ማለፉን አስመልክቶ ተጠሪው ያቀረቡት መስቀለኛ የሰበር ቅሬታ የሌለ ሲሆን፣ በዚህ ነጥብ ላይ የሥር ጣልቃ ገብ የሆነው አመልካች ቅሬታ ሊያቀርብ የሚችልበት የህግ አግባብ አይኖርም። በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመ በመሆኑና ይግባኝ ሰሚው የሐረሪ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም የሥር ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ጉድለት የሌለበት ነው በማለት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት አልተፈጸመበትም ብለናል። በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል።

**ውሳኔ**

1. የሐረሪ ህ/ክ/መ/ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 24684 በሐምሌ 28 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ፣ እንዲሁም የሐረሪ ህ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 07051 በመስከረም 28 ቀን 2016 ዓ.ን በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ያልተፈፀመበት በመሆኑ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1(ሀ) መሠረት ፀንቷል ።
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻቻሉ።

**ትዕዛዝ**

1. መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ፋ/ዘ

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
## የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ. 254781

ህዳር 27 ቀን 2017 ዓ/ም

**ዳኞች፡-** ሽመክት አሰፋ

እንዳሻው አዳነ

አለማየሁ ሹናራ

ተናኜ ጥላሁን

ዋዚሞ ዋሴራ

አመልካች፡- አቶ ደረጀ ለገሰ አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ሚሊተሪ ተራ ነጋዴዎች ማህበር ጠበቃ ሰለሺ ቀፀላ ቀረቡ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው። በዚሁ አግባብ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

**ፍርድ**

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች በጥቅምት 21 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 239592 በሐምሌ 27 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው።ጉዳዩ ከውል ውጪ ኃላፊነትን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው። በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር አመልካች ከሳሽ፣ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል።

አመልካች በሥር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ ከተከሳሹ ላይ የቤት ቁጥር 001/ኤ፣ የሱቅ ቁጥር F4-042C የሆነ በ3/07/2012 ዓ/ም በተደረገ ውል፣ በውላችን 4 እና 5 ተከሳሹ ህንጻና የተከራየሁትን ሱቅ ጥበቃ መድቦ ሊያሰራ ተስማምተናል። የጥበቃ ሥራው በስውር ካሜራ እንዲታገዝም አድርጓል። ይህ በእንዲህ እንዳለ በተከሳሽ የተመደበው ጥበቃ በቦታው እያለና

**ማስታወሻ፡** - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ካሜራው ባለበት በ14/5/13 ዓ/ም ሱቁ ተሰብሮ አልባሳት፣ ጫማዎች፣ የጠረጴዛ ጨርቆች በድምሩ ብር 519,812 ዋጋ ያለው ንብረት ስለጠፋብኝ ንብረቱ ከመያስገኘው ትርፍ ጭምር፣ ገንዘቡን ማግኘት ከነበረብኝ ንብረቱ ከጠፋበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር ከወጪና ኪሳራና የጠበቃ አበል ጋር እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

ተጠሪው በሰጠው መልስ ጎህ ከተባለው የጥበቃ ድርጅት ጋር ባደረግነው ውል ህንጻውን የምናስጠብቅ ቢሆንም ከሳሹ ንብረቱን እንዳያስጠብቅ በተከሳሽ አልተከለከለም፡፡ የከሳሹን ንብረት የሰረቁት ግለሰቦች በካሜራው ቅጂ ማንነታቸው ስለታወቀ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወንጀል ክስ ቀርቦባቸው በመ/ቁ. 271989 እየታየ ነው፡፡ ንብረት መጠበቅ ግዴታ የሌለበት ተከሳሽ ከከሳሽ ባልተረከበው ንብረት ኃላፊ ሊሆን ስለማይቻል ክሱ ውድቅ ይደረግልን፡፡ ተከሳሹ ሃላፊነት አለበት ከተባለ ደግሞ ከሳሹ ደረሰብኝ ያለው ጉዳት አልደረሰበትም፡፡ ከሳሹ ገዛኋቸው ያላቸው ዕቃዎች ሁሉም ሳይሸጡ ቆይተው ተወስደዋል ቢባል እንኳ በሱቅ ውስጥ የነበረው የብር 199,263 ዋጋ ያለው በመሆኑ ክሱ በከፍተኛ መጠን የተጋነነ ነው፡፡ ከሳሹ ነጋዴ ሆኖ እያለ ከሐምሌ 2011 እስከ ሚያዝያ 2012 ዓ/ም የተገዙ ያላቸውን ንብረቶች(ጨርቆች) ስርቆቱ እስከተፈጸመበት እስከ ጥር 2013 ዓ/ም ድረስ ከ10 ወር እስከ አንድ ዓመት ከስድስት ወር የተሸጠ ጨርቅ አለመኖሩ ሊታመን አይችልም፡፡ ክሱ በስርቆቱ ጊዜ በቦታው ባልነበረ የዕቃ መጠን፣ ያለአግባብ ለመበልጸግ ተጋኖ የቀረበ በመሆኑ ከሳሹ ደረሰብኝ ያለውን ያህል ጉዳት ያልደረሰበት በመሆኑና ዕቃው ያልተሸጠ በመሆኑ ቢሸጥ በእያንዳንዱ ዕቃ 45% አተርፍ ነበር ማለቱ መሠረት የሌለው ነው፡፡ የዕቃውን ዋጋ ቢያገኝ የተባሉትን እቃዎች ገዝቶ የሚሸጥ በመሆኑ የማይመለስ ጉዳት እንደደረሰበት አድርጎ ትርፉን ሊጠይቅ የሚችልበት አግባብ ስለሌለ ክሱ ወድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሮ፣ ጎህ የጥበቃ ድርጅት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 43 መሠረት በተከሳሽነት ጣልቃ ይግባልን በማለት ጠይቋል፡፡

ጎህ የጥበቃ ድርጅት ወደ ክርክሩ እንዲገባ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ሰጥቶ መጥሪያ ተልኮለት ስላልቀረበ ጣልቃ ገቡ በሌለበት ጉዳዩ ታይቷል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የሥር ፍ/ቤት ተከሰሹ ሃላፊነት አለበት? የለበትም? ኃላፊነት ካለበት ከሳሹ ምን ያህል ሊካስ ይገባል? በሚል ጭብጥ ይዞ የከሳሽን ምስክሮች የሰማ ሲሆን፣ ተከሳሹ የቆጠረው ምስክር ሆነ የሰነድ ማስረጃ የለም፡፡ የከሳሽ ምስክሮች በሰጡት ምስክርነት በክሱ የተዘረዘሩት ንብረቶች ከሳሹ እንደተሰረቁበት፣ የከሳሽን ሱቅ የሚያስጠብቀው ተከሳሹ እንደሆነና ከሳሽና ሌሎች ተከራዮች በግላቸው ማስጠበቅ እንደማይችሉ ያስረዱ ሲሆን፣ ፍርድ ቤቱ ክሱንና ማስረጃውን

ከመረመረ በኋላ በግራ ቀኙ ውል ላይ የጥበቃ አገልግሎት መስጠትን አስመልክቶ ያደረጉት ስምምነት የሌለ በመሆኑ ክርክሩ ከውል ውጪ ኃላፊነትን በሚመለከተው የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2028 መሠረት መታየት ያለበት ነው ካለ በኋላ፣ ተከሳሹ በከሳሽ ላይ ለደረሰው ጉዳት(ስርቆት) ቅድመ ጥንቃቄ ማድረጉን ወይም ቸልተኝነት እንደሌለበት ያላስረዳ በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2029 መሠረት ሃላፊ ነው በማለት ወስኗል፡፡

ጣልቃ ገቡን በተመለከተ ሃላፊነት እንዲጋራ ተከሳሽ ቢጠይቅም ከምን የመነጨ ሃላፊነት እንዳለበት ተከሳሽ ስላላስረዳ ሃላፊነቱ የተከሳሽ ነው ብሏል፡፡ የጉዳቱን መጠን በተመለከተ የተሰረቁትን ዕቃዎች ደረሰኝ ከሳሽ ያቀረበና 50% በላይ ትርፍ ሊያገኝ እንደሚችል ጭምር ስላስረዳና ተከሳሹ ግን ምንም አይነት ተቃራኒ ማስረጃ ስላላቀረበ ክስ የቀረበበትን ብር 519,812.08 ከ9% ወለድ ጋር ተከሳሽ ለከሳሽ እንዲከፍል በማለት ወስኖ ኪሳራውና ወጪ የመጠየቅ መብቱን ለከሰሽ ጠብቋል፡፡

በተጠሪ ይግባኝ ባይነት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሥር ፍርድ ቤቱን ውሳኔ በማሻሻል ሃላፊነትን በተመለከተ የሥር ፍርድ ቤቱ የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶ መጠንን በተመለከተ በሥር ፍርድ ቤት የተሰሙት ምስክሮች የአመልካች ሱቅ መሰረቁን ከማስረዳታቸው በቀር በክሱ የተዘረዘሩት ንብረቶችሁሉ የተሰረቁ ስለመሆናቸው ስላላስረዱ የከሳሹ ሱቅ በተሰረቀ ጊዜ የነበሩ ንብረቶችና ግምታቸው ተለይቶ ስላልታወቀ ንብረቶቹ የተገዙበት ደረሰኝ በመኖሩ ብቻ ከ10 ወር በፊት የተገዙ ንብረቶች ሁሉ ያልተሸጡና የተዘረፉ ናቸው የሚል መደምደሚያ ላይ ስለማያደርስ በርትዕ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1790/2 እና 2099 ብር 200,000 ካሳ ተከሳሽ ለከሳሽ ሊከፍል ይገባል በማለት የካሳውን መጠን ዝቅ በማድረግ ተከሳሽ ለከሳሽ ሊከፍል የሚገባው ብር 200,000፣ ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር ነው ካለ በኋላ ኪሳራና ወጪን በተመለከተ አመልካቹ ተሻሽሎ በተወሰነለት መጠን የመጠየቅ መብቱን ጠብቋል፡፡

አመልካች በሰኔ 21 ቀን 2016 ዓ/ም በተጻፈ ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይህን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ሲሆን ይዘቱም አመልካች ከተጠሪ በተከራየሁት ሱቅ ውስጥ ስርቆቱ በተፈጸመበት ጊዜ የነበሩት ዕቃዎች ዝርዝርና ዋጋቸው ብር 358,491፣ የትርፍ ህዳግ ተጨምሮበት አጠቃላይ ብር 519,812.08 መሆኑ በሰው ምስክርና በሰነድ ማስረጃ ተረጋግጦ ቀርቦ እያለና በተጠሪ በኩል ምንም አይነት ማስረጃ ሳይቀርብ በምንም ማስረጃ ሳይረጋገጥና የጠፋው ንብረት ምንነት፣ ብዛት፣አይነት እና ዋጋ በግልጽ እየታወቀ እንዲሁም የትርፍ ህዳግን በተመለከተም በሰው ምስክር አረጋግጠን እያለ በሰነድ ማስረጃ መረጋገጥ አለበት የሚል አስገዳጅ ድንጋጌ ሳይኖርና ፖሊስ የጠፉትን ንብረቶች ዝርዝር በግልጽ አስፍሮ ምርመራ ሲያደርግ መቆየቱ እየታወቀ የጠፉት ንብረቶች

ብዛት አይነትና ምንነት እንደማይታወቅ ተደርጎ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በርትዕ በመወሰን የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሳኔ ማሻሻሉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ተጠሪ ባከራየውና ጥበቃዎችን ቀጥሮ በኃላፊነት ስጠብቅ ከነበረው አመልካች ሱቅ ተሰብሮ የተሰረቀውን ንብረት እና ዋጋው በዝርዝር በቀረበው መሠረት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በማስረጃ አጣርቶ የሰጠውን ውሳኔ የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት በርትዕ ሊወሰን ይገባል በሚል አሻሽሎ የወሰነበትን አግባብ ከፍ/ብ/ህ/ቁ. 2153 እና ተከታታይ ድንጋጌዎች ይዘትና ትክክለኛ አፈጻጸም አንጻር ተጣርቶ ሊወሰን ይገባል በሚል በአብላጫ ድምጽ በተሰጠ ትዕዛዝ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በሐምሌ 26 ቀን 2016 ዓ/ም በተጻፈ የሰጡት መልስ ይዘት በአጭሩ የተሰረቀው የአመልካች እቃ አይነትና መጠን ምን እንደሆነ የቀረበ የቪዲዮ ማስረጃ የለም፡፡ ለፖሊስ የቀረበው ቢዲዮ የሚያሳየው ሌቦቹ ሱቁን ሰብረው የገቡና እቃ ያወጡ መሆኑን ብቻ ነው፡፡ ፖሊስም የመዘገበው አመልካች ጠፋብኝ ያለውን እንጂ ፖሊስ በራሱ ያረጋገጠውን አይደለም፡፡ አመልካቹ ተሰረቀብኝ ያለውን የእቃ አይነትና መጠን ለማስረዳት ያቀረበው ማስረጃ እቃዎቹ የተገዙበትን ደረሰኝ ሲሆን ይህም ስርቆቱ ከመረጸሙ ከአሥር እስከ አሥራ ዘጠኝ ወር በፊት የተገዙ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ እቃዎቹን አመልካች ገዝቶ የነበረ መሆኑ ቢረጋገጥም ስርቆት በተፈጸመበጽ ቀን እነዚህ እቃዎች መኖራቸው ግን አልተረጋገጠም፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ለክሱ በሰጠነው መልስ ላይ አመልካች በ2012 ዓ/ም ለገቢዎ ያሳወቀውን የሽያጭ መጠን እንዲሁም የሽያጭ ደረሰኝ ከገቢዎች ባሥልጣን እንዲቀርብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 145 መሠረት አመልክተን የነበረ ቢሆንም የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይህንን የተጠሪን ማስረጃ ሳያስቀርብ ውሳኔ በመስጠቱ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ላቀረብነው የይግባኝ ቅሬታ አንዱ ምክንያት ነበር፡፡ በመሆኑም ተገበ ማስረጃ ባልቀረበበት ሁኔታ ለ19 ወራት እቃው አልተሸጠም ነበር ብሎ ለማመን ያስቸግራል በማለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በርትዕ ውሳኔ መስጠቱ የሚነቀፍበት ምክንያት ባለመኖሩ ውሳኔው ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የግራቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ የቻልነው አመልካቹ ከተጠሪው ህንጻ ውስጥ በተከራዩት ሱቅ ውስጥ ተሰረቀብኝ ያሉትን ንብረት በተመለከተ በሱቁ ውስጥ የነበሩ ንብረቶች እንደተሰረቁባቸውና ተጠሪ ለንብረቶቹ መሰረቅ በጥፋት ላይ የተመሰረተ ኃላፊነት ባይኖርበትም ከውል ውጪ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ ግራ ቀኙን ያላከራከረና የሥር ፍርድ ቤትም በማስረጃ ያረጋገጠው ፍሬ ነገር ሲሆን፣ የተሰረቁት ዕቃዎች ስርቆቱ ከተፈጸመበት ጊዜ ከ10 ወር እስከ 19 ወራት በፊት ባሉት ጊዜያት ውስጥ የተገዙ መሆናቸውን የሚያስረዳ የሰነድ ማስረጃ ከመቅረቡ በስተቀር የተሰረቁትን እቃዎች አይነትና መጠናቸውን በተመለከተ በመለየት የቀረበ ማስረጃ እንደሌለ ከሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ይዘት መረዳት የሚቻል ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች በሱቅ ውስጥ የነበሩ እቃዎች እንደተሰረቁባቸው ቢታወቅም አይነትና መጠናቸው ግን ባለመታወቁ አመልካቹ ከስርቆቱ ጊዜ ከ10 እስከ 19 ወራት በፊት የገዙአቸው እቃዎች በሙሉ ሳይሸጡ ስርቆቱ እስከ ተፈጸመበት ቀን ድረስ በሱቁ ውስጥ ነበሩ ብሎ መደምደም ምክንያታዊ ስለማይሆንና እንዲህ በሆነና የደረሰውን ጥፋት ለመገመት የማይቻል በሆነ ጊዜ ዳኞች ሊከፈል የሚገባውን የካሳ ልክ መወሰን እንደሚችሉ የተደነገገ በመሆኑ ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከዚህ አንጻር የደረሰበት ድምዳሜና የካሳ መጠኑንም ዝቅ በማድረግ በርትዕ መወሰኑ ከላይ የተመለከተውን የህግ ድንጋጌ መሠረት ያደረገ በመሆኑ ውሳኔው መሠረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 239592 በሐምሌ 27 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ያልተፈጸመበት በመሆኑ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1(ሀ) መሠረት ፀንቷል ፡፡ በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻቻሉ፡፡

## ትዕዛዝ

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፣ ይመለስ፡፡

ፉ/ዘ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መዝገብ ቁጥር - 254878

ቀን - 30/03/2017 ዓ/ም

ዳኞች - ሽመክት አሰፋ

እንዳሻው አዳነ

አለማየሁ ሹናራ

ተናኜ ጥላሁን

ዘውዲቱ ታደሰ

አመልካች - የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ደቡብ ምዕራብ ሪጅን አልቀረቡም

ተጠሪዎች - 1. ወ/ሮ አማረች የሊሶ አልቀረቡም

2. አቶ ስንሻው አስረስ ቀረቡ

3. አቶ አካሉ ታደሰ አልቀረቡም

መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው ለምርመራ ስለሆነ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የተጀመረው ዳውሮ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት አመልካች ተከሳሽ 1ኛ ተጠሪ፣ ከሳሽ 2ኛ ተጠሪ ጣልቃ ገብ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ከሳሽ በተከሳሽ ላይ ያቀረቡት ክስ ዝርዝር በአጭሩ የተከሳሽ ንብረት የሆነው የኤሌክትሪክ መስመር መሰቀል ከነበረበት ደረጃውን ዝቅ አድርጎ በመሰቀሉ ምክንየቃት ሟችን ይዞት በአስፋለት መንገድ ላይ በመጣል በመግደሉ ሟች የመኪና ረዳት ሰራተኛ ስለሆነ

በየቀኑ 300.00 ብር የሚያገኝ በመሆኑ ለእናቱ በየቀኑ ብር 150.00 የሚሰጠው ገቢ የተቋረጠ ስለሆነ የሟች እድሜ 23 አመት በመሆኑ ቀሪ ወደ ፊት የሚኖረው 37 አመት በመሆኑ በቀን ገቢ

1. 150.00 በወር 4,500 ብር በአመት 54,000.00 የ 37 አመት ብር 1,998,000.00 (አንድ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ዘጠና ስምንት ሺህ ብር) ካሳ እንዲከፍል፣
2. የሞራል ካሳ 1,000.00 (አንድ ሺህ ብር)
3. የሟች ለቅሶና የቀብር ወጪ ብር 76,820.00 አጠቃላይ ድምር ብር 2,278,970.00 (ሁለት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሰባ ስምንት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰባ ብር ከጠበቃ ወጪ ጋር እንዲከፍል የሚል ነው።

ለተከሳሽ ክሱ ደርሶት የበኩሉን መልስ ያቀረበ ሲሆን ይዘቱ በአጭሩ የኤሌክትሪክ መስመሩ ያልረገበና ደረጃውን የጠበቀ ነው። ሟች የሞተው በኤክትሪክ ገመድ ተይዞ ሳይሆን በተሽከርካሪው ጥፋት መሆኑን የደረሰው ጉዳት በኤክትሪክ አደጋ የደረሰ መሆኑን የህክምና ማስረጃ አያስረዳም። የመኪናው ከፍታ እና የሟች ቁመት ተጨምሮ የኤሌክትሪክ መስመር ተዘርግቶ ያለበት ቦታ የደረሰ በመሆኑ የደረሰው ጉዳት ከሟች ጥፋት የደረሰ መሆኑን 3ኛ ወገን ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር ጠይቋል። የካሳ ጥያቄውም ቢሆን ሰርቶ መብላት የሚችል መሆኑን ሟች ከመሞቱ በፊት ገቢ ያልነበረው መሆኑን የካሳ መጠኑ የተጋነነ መሆኑን የሟች እድሜ በሀኪም ያልተረጋገጠ ስለሆነ የከሳሽ ክስ ውድቅ እንዲደረግ በማለት ተከራክሯል። የጣልቃ ገብ መልስ አደጋ የደረሰው በጣልቃ ገብ ሳይሆን በኤሌክትሪክ አደጋ የደረሰ መሆኑን ይህንን የሚያስረዳ ከዳግማዊ ሚኒልክ ሆስፒታል የሀኪም ማስረጃ የቀረበ ስለሆነ ጣልቃ ገብ አላፊነት የለም ተብሎ እንዲወሰን የሚል መልስ አቅርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል። በተጨማሪ አመልካች የመኪናው ባለቤት ወደ ክርክሩ ውስጥ እንዲገባ አመልክተው ፍርድ ቤቱም ለመኪናው ባለቤት መጥሪያ እንዲያደርስ ቢያዝም መጥሪያ ለመኪናው ባለቤት በአግባቡ ባለመድረሱ ታልፏል። የግራ ቀኙ የፅሁፍ እና የቃል ክርክር ከተጠናቀቀ በኃላ በግራ ቀኙ በኩል ምስክሮች ቃል ተሰምቷል። የከሳሽ ምስክሮች የኤሌክትሪክ ገመድ ዝቅ ብሎ ስለነበረ ሟችን ይዞት መወርወሩን፣ ሟች የመኪና ረዳት ሆኖ በቀን ብር 150.00 ለከሳሽ እናት የሚሰጥ መሆኑን፣ የሟች እድሜ 23 አመት መሆኑን የሞተበት ምክንያት በሀኪም የተረጋገጠ መሆኑን አስረድተዋል። የተከሳሽ ምስክሮች ሟች በሎደር ላይ ወጥቶ በእርጥብ እንጨት መብራት ሲነካ መሞቱን ጥፋቱ የሟች መሆኑን አስረድተዋል። የጣልቃ ገብ ምስክሮች የመብራት ሀይል ተሸካሚው 6.65 ሜትር መሆኑን አደጋው መኪናው ከሄደ በኃላ የደረሰ መሆኑን የመብራት ሽቦ ዝቅ ብሎ ስለነበር ከመብራት ጋር ኮንታክት ፈጥሮ ሟች መሞቱን አስረድተዋል።

ከዳግማዊ ሚኒሊክ ሆስፒታል የቀረበ የሀኪም ማስረጃ ለሟች ሞት ምክንያት የሆነው በመብራት ኃይል ወደ ልቡና ሌሎች አካላት ተሰራጭቶ መሆኑ ተረጋግጧል። የግራ ቀኙ ማስረጃ ቃል ተሰምቶ ከተጠናቀቀ በኃላ ፍርድ ቤቱ መዝገቡን መርምሮ ለሟች መሞት ተከሳሽ ብቻውን አላፊ ነው በማለት የካሳ መጠንን በተመለከተ የካሳው ጠያቂ የሟች እናት የከሳሽ እድሜ 40 አመት በመሆኑ የእድሜ ጣሪያ 60 አመት በመያዝ ቀሪ 20 አመት ከሳሽ ከሟች ልጇዋ የምታገኘው ገቢ የተቋረጠ ስለሆነ ብር 1,080,000.00 (አንድ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ሚሊዮን ሰማኒያ ሺህ ብር) እና የሞራል ካሳ 1,000.00 (አንድ ሺህ ብር)፣ የነዳጅ ወጪ 2,684.00 (ሁለት ሺህ ስድስት መቶ ሰሚኒያ አራት ብር)፣ የሬሳ ሳጥን ወጪ 10,000.00 (አስር ሺህ ብር)፣ የቀብር ወጪ ብር 49,360.00 (አርባ ዘጠኝ ሺህ ሶስት መቶ ስልሳ ብር)፣ የለቅሶ ወጪ ብር በርትዕ 178,750.00 (አንድ መቶ ሰባ ስምንት ሺህ ሰባት መቶ ሀምሳ ብር) በአጠቃላይ ብር 1,321,791.00 (አንድ ሚሊዮን ሶስት መቶ ሀያ አንድ ሺህ ሰባት መቶ ዘጠና አራት ብር) ተከሳሽ ለከሳሽ እንዲከፍሉ ሲል ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ቅሬታቸውን ለደቡብ ምዕራብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ፍርድ ቤቱ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ውሳኔ አፅንቶታል፡፡

የአሁን ሰበር ቅሬታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ የቀረበ ሲሆን የሰበር ቅሬታው ይዘት በአጭሩ 2ኛ ተጠሪ የመኪና አሽከርካሪ ሹፌር ከመጠን በላይ በሆነ ከፍታ በጭነት መኪና ላይ ሎደር ጭኖ ሟች በመኪና ላይ አሳፍሮ እየተጓዘ የደረሰ አደጋ ስለሆነ ከሟች ሞት ምክንያት የሆነው 2ኛ ተጠሪ መሆኑን፣ ለሟች መሞት ምክንያት የሆነው 2ኛ ተጠሪ በመሆኑ ለጉዳቱ አላፊ ሊሆን የሚገባው 2ኛው ተጠሪ ሆኖ ሳለ የስር ፍርድ ቤት 2ኛ ተጠሪን ከአላፊነት ውጪ ማድረጉ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ነው፡፡ አሽከርካሪ በአሽከርካሪነት ስራው ላይ ማድረግ የሚገባውን ጥንቃቄ ሳያደርግ ቀርቶ በሌላ ሰው ላይ የሞት አደጋ ያደረሰ ሹፌር በህግ የመጠየቅ መብትን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 55649 አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠ በመሆኑ የተሽከርካሪው ባለቤት ከአሽከርካሪው ጋር በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ ነው ተብሎ መወሰን ሲገባ ሳይወሰን አመልካችን ብቻ አላፊ ማድረጉ ስህተት ነው፡፡ የመኪና ባለቤት ወደ ክርክሩ ውስጥ ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር አመልክተን የፍርድ ቤት መጥሪያ ላለመቀበል ራሱን የሸሸገ በመሆኑ ጉዳዩ በሌለበት መወሰን ሲገባው ይህ መታለፉ ስህተት ነው፡፡ ሟች በጭነት መኪና ላይ በተጫነው ሎደር ማሽን ላይ ወጥቶ ኤሌክትሪክ ሽቦ ተወጥሮ ያለውን ድረስ እጁን ዘርግቶ በእርጥብ ማገር እንጨት መንካቱ የተጎጂው ጥፋት መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የስር ፍርድ ቤት አመልካችን አላፊ ማለቱ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ስለሆነ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሮ እንዲወሰን ይህ የማይቻል ከሆነ ክርክሩ በድጋሚ እንዲካሄድ እንዲወሰን የሚል ነው፡፡

ይህ ችሎት በስር ፍርድ ቤት በማስረጃ ተረጋገጠ ከተባለው ፍሬ ነገር የአሁኑ 3ኛ ተጠሪ (የመኪናው ባለቤት) ወደ ክርክሩ እንዲገባ ተጠይቆ መጥሪያው በአግባቡ ስለመድረሱ ማረጋገጫ አልቀረበም ተብሎ ከመታለፉ አንፃር ለጉዳቱ የአሁኑ ተጠሪ ብቻውን ኃላፊነት አለበት ተብሎ መወሰኑ አጥፊ ሳይሆን አላፊ ስለመሆኑ በፍ/ብሄር ህጉ የተመለከቱ ድንጋጌዎችና ክርክሩ የሚመራበትን ስርአት መሰረት ያደረገ መሆን አለመሆኑን አጣርቶ ለመወሰን ሲባል በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ 2ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 28(3) መሰረት ያስቀርባል በመባሉ 1ኛ ተጠሪ በ 17/10/2016 ኢ.ም በተፃፈ 03 ገፅ መልስ አቅርበው ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡ ሙሉ ቃሉ በአጭሩ አመልካች በ 3ኛ ተጠሪ ላይ ያቀረበው አቤቱታ ለችሎቱ ሊቀርብ አይገባም፣ ለ 3ኛ ተጠሪ መጥሪያ አመልካች ማድረስ ባለመቻሉ 3ኛ ተጠሪ ከክስ እንዲወጣ ማድረጉ አግባብ ነው፡፡ የአመልካች ሽቦ ረግቦ ያለው ከመኪና ጋር ኮንታክት ፈጥሮ ሟችን የገደለ ስለመሆኑ በማስረጃ

የተረጋገጠ ስለሆነ በስር ፍርድ ቤት አመልካችን ብቻ አላፊ ማድረጉ በአግባቡ ነው፡፡ የአመልካች ማስረጃ ክሱን ያላስተባበለ ስለሆነ የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ፍርድ እንዲፀናልኝ የሚል ነው፡፡ 2ኛ ተጠሪ በ 17/10/2016 ዓ.ም በተፃፈ 02 ገፅ መልስ አቅርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡ ይዘቱ በአጭሩ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት 2ኛ ተጠሪን በተመለከተ ለማጣራት የያዘው ጭብጥ አለመኖሩን፣ 2ኛ ተከሳሽ በወንጀል ተከስሼ ነፃ መውጣቴን በስር ፍርድ ቤት 2ኛ ተጠሪ የፍ/ብሄር ኃላፊነት የለበትም በማለት የሰጠው ፍርድ በአግባቡ ስለሆነ እንዲያፀናልኝ የሚል ነው፡፡ ለ 3ኛ ተጠሪ አመልካች በተደጋጋሚ መጥሪያ እንዲያደርስ ታዞ ባለማድረሱ በ 3ኛ ተጠሪ ላይ አመልካች ያቀረበው ቅሬታ ቀሪ እንዲሆን በ 06/02/2017 ዓ.ም በዋለው ችሎት ታዟል፡፡ አመልካች በ 02/11/2016 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልሳቸውን የሰበር ቅሬታቸውን በማጠናከር አቅርበው ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ በተገለፀው መሰረት የተጠቃለለ በመሆኑ እኛም ለሰበር ቅሬታ መነሻ የሆነውን ፍርድ፣ በግራ ቀኙ በኩል የቀረበውን ክርክር፣ ይህ ችሎት ካስቀረበው ጭብጥ አንፃር ለ 3ኛ ተጠሪ የመኪና ባለቤት መጥሪያ በአግባቡ ስለማድረሱ መግለጫ አላቀረበም ተብሎ መታለፉ አመልካች ብቻውን አላፊነት አለበት ተብሎ መወሰኑ አጥፊ ሳይሆን አላፊ ስለመሆን ህግ ክርክሩ የተመራበት ስርአት መሰረት ያደረገ መሆን አለመሆኑን አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር አገናዝበን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

መርምረን እንደተረዳነው ከሆነ የ 1ኛ ተጠሪ ወ/ሮ አማረች የሊሶ ዳኘነት ጥያቄ የአመልካች ንብረት የሆነው ኤሌክትሪክ መስመር ልጃቸውን በመግደሉ በፍ/ብ/ህ አንቀፅ 2069 መሰረት አላፊ ስለሆኑ የጉዳት ካሳ እንዲከፍሉ የሚል ነው፡፡ የአመልካች ክርክር የ 1ኛ ተጠሪ ልጃቸው የ 3ኛ ተጠሪ ንብረት በሆነው መኪና ላይ ወጥቶ በእርጥብ እንጨት የኤሌክትሪክ መስመር ነክቶ የሞተ ስለሆነ ጥፋቱ የመኪናው ባለቤት እና የሟች ስለሆነ አላፊነት የለብኝም በማለት ይከራከራል፡፡ የ 1ኛ ተጠሪ ምስክሮች የኤሌክትሪክ መስመር ይዞ ልጃቸው የሞተ መሆኑን ተጠሪ የሚኖሩት ልጃቸው በሚሰጣቸው ገቢ መሆኑን ሟች የመኪናው ረዳት መሆኑን አስረድተዋል የስር 1ኛ ጣልቃ ገብ ስንሻው አስረስ ምስክሮች የመብራት ሽቦ መስቀል ከነበረበት ደረጃ ዝቅ ብሎ ስለተዘረጋ መኪና ሲያልፍ ኮንታክት ፈጥሮ ሟችን የገደለ ስለመሆኑ አስረድተዋል፡፡ የአመልካች ምስክሮች ሟች በሎደር መኪና ላይ ወጥቶ በእርጥብ እንጨት መብራት ሲነካ መሞቱን ያስረዱ ቢሆን በቦታው ያልነበሩ የአይን ምስክሮች ባለመሆናቸው የስር ፍርድ ቤት አልተቀበለውም፡፡ አመልካች ለሟች መሞት ምክንያት የሆነው የመኪናው ባለቤት የሆነው አቶ አካሉ ታደሰ እና ሟች ነው በማለት ቢከራከሩም አመልካች የኤሌክትሪክ መስመሩን ሲዘረጋ ሰውና እንስሳት በማይደርሱበት ሁኔታ ደረጃውን ጠብቆ ከፍ አድርጎ መዘርጋት ሲገባው ደረጃውን ሳይጠብቅ ዝቅ አድርጎ በመዘርጋቱ መኪናው በሚያልፍበት ጊዜ ሟች ነክቶ ጉዳት ያደረሰ ስለመሆኑ ማስረጃ የመመዘንና የመመርመር ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ የመኪናው ባለቤት ለሟች መሞት ምክንያት ስለመሆኑ በአመልካች በኩል አልተረጋገጠም፡፡ ሟች የሞተው ከኃላ በመኪናው ላይ በመውጣቱ ከኤሌክትሪክ መስመር ጋር ኮንታክት ፈጥሮ የሞተ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

ቢሆንም ከመነሻው ኤሌክትሪክ መስመር የተዘረጋው መኪናው በሚደርስበት ሁኔታ ዝቅ ተደርጎ ከመዘርጋቱም ሌላ የኤሌክትሪክ መስመር ሽቦ ኃይል እንዳይተላለፍ በፕላስቲክ መሸፈን ሲገባው ከአደጋ ለመከላከል በፕላስቲክ ባለመሸፈኑ መነሻ የደረሰ ጉዳት በመሆኑ አመልካች መውሰድ የሚገባውን ጥንቃቄ ባለመውሰዱ ምክንያት በሟች ላይ ያስከተለውን የሞት አደጋ አመልካች ለብቻው አላፊ ነው መባሉ በአግባቡ ሆኖ አግኝተናል፡፡ አንድ ሰው የሚፈነዳ ወይም መርዝ የሚሆኑ ቅመማት በስራ ላይ በማዋል ወይም በማከማቸት ወይም ከፍተኛ ጉልበት ያለው የኤሌክትሪክ መስመር በመዘርጋት ወዘተ አደጋ ያደረሰ እንደሆነ አጥፊ ሳይሆን አላፊ እንደሆነ በፍ/ብ/ህ አንቀፅ 2069(1) ስር ተደንግጓል፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይ አመልካች የኤሌክትሪክ መስመሩን ሲዘረጋ ደረጃውን በጠበቀ ሁኔታ ከፍ አድርጎ መዘርጋት ሲገባው መኪናን በማያሳልፍ ሁኔታ በመዘርጋቱ ከኃላ በመኪናው ላይ ያለው ረዳት ሹፌር ከኤሌክትሪክ መስመሩ ጋር ተነካክቶ የሞተ ስለሆነ ከመነሻው አመልካች የኤሌክትሪክ ሽቦ ጉዳት እንዳያደርስ የአደጋ መከላከያ ፕላስቲክ ሽፍኖ ቢሆን ኖሮ አደጋ አይደርስም ነበር አመልካች ማድረግ የሚገባውን ጥንቃቄ አላደረገም፡፡ አመልካች ከደረሰው ጉዳት በኃላፊነት የሚጠየቀው በሟች ጥፋት ጉዳቱ የደረሰ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ህ አንቀፅ 2086(2) መሰረት ማስረዳት ሲችል ነው፡፡ በሟች ጥፋት የደረሰ ጉዳት ስለመኖሩ አላስረዳም፡፡ ከመነሻውም ቢሆን የኤሌክትሪክ መስመሩ የተዘረጋው የከፍታ ደረጃውን በጠበቀ ሁኔታ ሳይሆን መኪና በማያሳልፍበት ሁኔታ ዝቅ ተደርጎ የተዘረጋ ከመሆኑም ሌላ አደጋ እንዳያደርስ ደንብ ቁጥር 49/1991 አንቀፅ 35 መሰረት ስለ ኤሌክትሪክ መስመሮች ደህንነት የደነገገውን በማያሟላ ሁኔታ ተዘርግቶ የነበረ መሆኑን በአንቀፅ 41(1) መሰረት የተዘረጋው የኤሌክትሪክ መስመር የአደጋ መከላከያ ፕላስቲክ ተሸፍኖ የነበረ መሆኑን አመልካች ያላስረዳ በመሆኑ የፌዴራል ጠቅለቃይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 57904 በቅፅ 11 ላይ የሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሰረት ለጉዳቱ ሙሉ በሙሉ አመልካች አላፊ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤቶች የደረሱበት ድምዳሜ የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ሲጠቃለል የመኪናው ባለቤት ጥፋትም ሆነ አጥፊ ሳይሆን አላፊ የሚሆንበት መንገድ ባለመገኘቱ በስር ፍርድ ቤት መጥሪያ አመልካች በአግባቡ ባለማድረሱ ቀርቦ ባይከራከርም የሚያስጠይቅ ሁኔታ ባለመኖሩ በዚህ ነጥብ ላይ አመልካች ያነሳውን ቅሬታ አልተቀበልነውም፡፡ የአመልካች ንብረት የሆነው የኤሌክትሪክ መስመር መኪና በሚያልፍበት ሁኔታ ዝቅ ተደርጎ የተዘረጋ በመሆኑ ሟች ከኃላ በመኪናው ላይ ያለውን ነክቶ የገደለ በመሆኑ የኤሌክትሪክ ሽቦ ጉዳት እንዳያደርስ የአደጋ መከላከያ ፕላስቲክ መሸፈን ሲገባው ያልሸፈነ በመሆኑ በሟች ላይ የሞት አደጋ ስላደረሰ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 57904 ቅፅ 11 ላይ ከሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉምና በፍ/ብ/ህ አንቀፅ 2069(1) መሰረት ለደረሰው ጉዳት አመልካች ሙሉ በሙሉ አላፊ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ፍርድ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ባለመኖሩ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

1. ዳውሮ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 15768 በቀን 14/10/2015 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ እና የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤትይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 18568 በቀን 18/01/2016 ኢ.ም የሰጠው ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የሌለው ስለሆነ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስነ ስርአት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9(1)(ሀ) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት በቀን 07/03/2016 ኢ.ም የተሰጠው እግድ ተነስቷል ይፃፍ፡፡
4. በዚህ ችሎት የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻቻሉ፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ፋ/ዘ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

**የሰ/መ/ቁ/255137**

ኅዳር 26 ቀን 2017 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ብርቅነሽ እሱባለዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

**አመልካች** - አቶ ከበደ ገ/ጊዮርጊስ አኅናፍር ከጠበቃ ኢሊያስ ጋር ቀርበዋል

**ተጠሪ** - ይርጋለም አዲስ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ጠበቃ ገነት መላኩ ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የስራ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን፣ ክርክሩ በተጀመረበት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ባቀረቡት ክስ በተጠሪ ድርጅት በኦፐሬሽን መምሪያ ኃላፊ ስር በብርድ ልብስ ማምረቻ ክፍል ኃላፊነት ከነሐሴ 16 ቀን 2003 ጀምሮ በወር ብር 18,551.00 ደመወዝ እየተከፈላቸዉ ሲያገለግሉ ቆይተዉ ተጠሪ ሰኔ 22 ቀን 2014 ዓ.ም ከህግ ዉጪ ከስራ ያሰናበታቸዉ መሆኑን ጠቅሰዉ ክፍያ የዘገየበትን ቅጣት ጨምሮ ህገ ወጥ የስራ ስንብት የሚያስከትላቸዉን የተለያዩ ክፍያዎች በድምሩ ብር 253,530.00 ተጠሪ እንዲከፍል እና የስራ የምስክር ወረቀትም እንዲሰጣቸዉ ይወሰንላቸዉ ዘንድ የጠየቁትን ዳኝነት መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡

ተጠሪ ለክሱ በሰጠዉ መልስ አመልካች የስራ መሪ ናቸዉ የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማስቀደም ስንብቱ ህጋዊ ነዉ የሚልባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር ክሱ ዉድቅ ሆኖ ይወሰንለት ዘንድ ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች በህጉ አግባብ የስራ መሪ መሆናቸዉን የሚያሳይ ማስረጃ በክርክሩ መሠረት ተጠሪ ያላቀረበ መሆኑን ጠቅሶ ተጠሪ በዚህ ረገድ ያቀረበዉን መቃወሚያ ዉድቅ በማድረግ የፍሬ ነገር ክርክሩን መርምሮ ተጠሪ አመልካችን ከስራ ያሰናበተበት አግባብ ህገ ወጥ ነዉ በሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ የተለያዩ ክፍያዎችን ለአመልካች እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪ በዚህ ዉሳኔ ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን፣ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ በበኩሉ የይግባኝ አቤቱታዉን አስቀርቦ ከመረመረ በኋላ በተጠሪ ድርጅት ለአመልካች የተሰጠዉ የስራ መዘርዘር ተራ ቁጥር 8(17) ላይ አመልካች የመመሪያዉን የሰዉ ኃይል እንደሚያሟላ፣ የቅጥርና የዕድገት ዝዉዉር እና የድስፕሊን ጉዳዮችን እንደሚከታተል እና እንደሚወስን የሚገልጽ መሆኑና አመልካችም በዚህ የስራ መዘርዝር ላይ ተቃዉሞ ያላቀረቡ መሆኑን ጠቅሶ አመልካች በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 2(10) እንዲሁም ሰበር በተለያዩ መዛግብት ላይ በሰጠዉ አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሠረት የስራ መሪ ናቸዉ በሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ የስር ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካች ህዳር 12 ቀን 2016 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ አመልካች በተጠሪ ድርጅት ዉስጥ ለረዥም ዓመታት በሰሩባቸዉ ወቅት ሠራተኞችን በፊርማቸዉ መቅጠራቸዉን፣ ማሰናበታቸዉን፣ ማዛወራቸዉ፣. ዕድገት መስጠታቸዉን የሚያሳይ ማስረጃ ተጠሪ ባላቀረበበት ሁኔታ አመልካች የስራ መሪ ናቸዉ በሚል በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት መሆኑን ጠቅሰዉ ታርሞ ይወሰንላቸዉ ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የሰበር አቤቱታዉ በሰበር ችሎት ተመርምሮ ያስቀርባል በመባሉም ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ ጥሪ ተደርጎለታል፡፡ በዚህም መሠረት ተጠሪ ሰኔ 27 ቀን 2016 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች የስራ መሪ ስለሆኑ ጉዳያቸዉ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ሊታይ አይገባዉም በሚል በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት መሆኑን ጠቅሶ ጸንቶ እንዲወሰንለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡ አመልካች ሐምሌ 11 ቀን 2016 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል፣ ይህ ችሎትም በስር ፍርድ ቤት በተሰጠ ዉሳኔ ላይ የተፈጸመ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡

እንደመረመረዉም በአሠሪና ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 2(10) ላይ እንተመለከተዉ አንድ ሠራተኛ የስራ መሪ ነዉ ለማለት ከሌሎች በህግ ወይም እንደ ድርጅቱ የስራ ጠባይ በአሠሪዉ በተሰጠዉ የዉክልና ስልጣን መሠረት የስራ አመራር ፖሊሲዎችን የማዉጣትና የማስፈጸም ስልጣን ያለዉ ወይም ሠራተኛን የመቅጠር፣ የማዘዋወር፣ የማገድ፣ የማሰናበት ወይም የመመደብ ተግባሮችን ለማከናወን ስልጣን ያለዉ ሰዉ እንደሆነ ይደነግጋል፡፡ በተያዘዉ ጉዳይ ከድርጅቱ በተሰጣቸዉ የስራ መዘርዝር መሠረት አመልካች የሰዉ ኃይል የማሟላት፤ የቅጥር፣ የዕድገት፣ የዝዉዉር እና

የድስፐሊን ጉዳዮችን የመከታተል እና የመወሰን ስልጣን የተሰጠዉ ስለመሆኑ በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ አመልካችም ቢሆን በስራ መዘርዘሩ እነዚህን የማከናወን ስልጣን አልተሰጠኝም የሚል ክርክር የላቸዉም፡፡ በዚህ ረገድ የአመልካች ክርክር በድርጅቱ ስሰራ በቆየሁበት ጊዜ ከእነዚህ ተግባራት ዉስጥ አንዱንም አከናዉኜ አላዉቅም፤ ተጠሪም ይህን በማስረጃዉም አላስረዳም የሚል ይዘት ያለዉ ነዉ፡፡

ይሁንና በአሠሪዉ ድርጅት ለሠራተኛዉ የተሰጠ የስራ መዘርዝር አንድን ሠራተኛ የስራ መሪ የሚያሰኙትን ተግባራት አስመልክቶ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጁ ላይ የተመለከቱትን ተግባራት ማከናወን እንዲችል ስልጣን የሚሰጥ መሆኑ ከተረጋገጠ፣ ሠራተኛዉ ስራዉን በተግባር አለማከናወኑ ሠራተኛዉ የስራ መሪ አይደለም በሚል ድምዳሜ ላይ የማያደርስ ስለመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 196970 (ያልታተመ) ላይ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ ለአመልካች የተሰጣቸዉ የስራ መዘርዝር በባህሪዉ አንድ ሠራተኛ የስራ መሪ ነዉ ሊባል የሚችልበትን አስመልክቶ በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 2(10) ላይ ከተመለከቱት ዉስጥ ቢያንስ አንዱን እንዲያከናዉን ስልጣን የሚሰጠዉ መሆኑ ከተረጋገጠ ሠራተኛዉ በተግባር ስራዉን አለማከናወኑ ሠራተኛዉ የስራ መሪ እንዳይባል ምክንያት ሊሆን የሚችል ባለመሆኑ፣ በዚህ ረገድ አመልካች የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት ያለዉ አይደለም፡፡

በሌላ በኩል በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ መንግስት እና ህገ መንግስቱን መሰረት አድርጎ በወጣው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሰረት ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው የዳኝነት ሥልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸውን ማናቸውንም የመጨረሻ ዉሳኔዎችን መርምሮ ማረም ስለመሆኑ የህገ መንግስቱ አንቀጽ 80(3/ሀ)) እና የአዋጁ አንቀፅ 10 ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት እንደሆነ በአዋጁ የትርጉም ክፍል በአንቀጽ 2(4) ስር በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ በዚህ መሠረት አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ተብሎ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችለዉ ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ ዉሳኔ በአዋጁ አንቀጽ 2(4) ስር ከተመለከቱት ሁኔታዎች ዉስጥ ቢያንስ አንዱን የሚያሟላ ሆኖ ዉጤቱም ፍትሕን የሚያዛባ ጉልህ ስህተት ያለበት ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ ከድንጋጌዎቹ አጠቃላይ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

ከዚህ ሁሉ አንፃር ሲታይ አመልካች የስራ መሪ ናቸዉ በሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በመሻር በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠዉ ዉሳኔ የተረጋገጠዉን ፍሬ ነገር፣ ለጉዳዩ አግባብነት ያለዉን ህግ እና ከላይ የተመለከተዉን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አስገዳጅ የህግ ትርጉም ያገናዘበ ነዉ ከሚባል በስተቀር በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ዉሳኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 296483 ላይ ጥቅምት 06 ቀን 2016 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ በሰበር ሥ/ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1) መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

ፋ/ዘ

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ.መ.ቁ255173

ቀን 27/3/2017

ዳኞች፡ ሺመክት አሰፋ

እንዳሻው አዳነ

ተናኜ ጥላሁን

ዋዚሙ ዋሴራ

ዘውዲቱ ታደሰ

አመልካቾች፡ 1. አቶ ደፋር ወርቁ

2. አቶ ገረመው ወርቁ } አልቀረቡም

3. አቶ ደመረ ቀፀላ

ተጠሪዎች፡ 1. ወ/ሮ ጂቱ ከበደ

2. አቶ አመንቴ ከበበው } አልቀረቡም

3. አቶ ሀብተማርያም አመንቴ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ይህ የሰበር ቅሬታ ሊቀርብ የቻለው  የአሁን አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት ተከሳሾች የሆኑት የኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 97630 በቀን 08/09/2015ዓ.ም  የሰጠውን ውሳኔ በመሻር ሰጠውን ውሳኔ በማፅናቱ  ቅር በመሰኘታቸው ነው፡፡ የአሁን አመልካቾች ተከሳሾች  የአሁን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ከሳሾች  የነበሩ ሲሆን 3ኛ ተጠሪ ወደ ክርክሩ እንደገባ በተከሳሾች ጥያቄ ፍርድ ቤት አዞ ወደ ክርክቱ የገባ  ነው፡፡ ከሳሾች ያቀረቡት ክስ ይዘትም በገበረ ጉራቻ ከተማ ቀበሌ 01 በ1ኛ ከሳሽ ስም ተመዝግቦ የሚገኘውን 434 ካሬ ሜትር ይዞታ ላይ ያለ ቤታችንን ጣልቃ ገብ ለሆነው ለልጃችን አቶ ሀብተማርያም አመንቴ እንዲያስተዳድርልን ውክልና የሰጠነው ቢሆንም እሱ ግን በ2002ዓ.ም በወቅቱ የገርበ ጉራቻ ከተማ አስተዳደር ባለስልጣናት ከሆኑት ተከሳሾች ጋር በመስማማት በተሰጠው ውክልና ቤቱን ከ1ኛ ከሳሽ በቀን 24/2/2002ዓ.ም እና 16/3/2002 ዓ.ም የገዛ በማስመሰል ተከሳሾች ወደ ስሙ እንዲያዛውሩለት በማድረግ በቤቱ ከባንክ ብር ተበድሮበት እዳውን መክፈል ባለመቻሉ ቤቱ በሀራጅ ተሽጦ ወደ ሶስተኛ ወገን ተላልፏል፡፡ በ2002ዓ.ም የቤቱ ዋጋ 228,690 ብር እንዲሁም በአሁን ሰአት የቤቱ ዋጋ 3,050,000 ብር ነው፡፡

ተካሾች ስልጣናቸውን ተጠቅመው ቤታችንን  ያሳጡን መሆኑ በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 352134 በቀን 16/03/2014ዓ.ም ተረጋግጦ  የጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጠባቸው በመሆኑ  ላደረሱብን ጉዳት የቤቱን ዋጋ 3,050,000 ብር በጋራ እና በተናጠል ሆነው እንዲከፍሉን ውሳኔ ይሰጥልን በማለት ክሳቸውን አቅርበዋል፡፡ ይህም ክስ ለተከሳሾች የደረሰ ሲሆን ተከሳሾችም መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ የመልሳቸውም ይዘት ከሳሾች ከዚህ ክስ በፊት ቤቱ በጨረታ በሚሸጥበት ጊዜ ቤቱ  የእኛ ነው  በማለት ተቃውሞ ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በ2004 ዓ/ም በመዝገብ ቁጥር 34441 እንዲሁም ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 140827 አቅርበው ውድቅ የተደረገባቸው በመሆኑ አሁን ላይ በዚህ ጉዳይ ክስ ሊያቀርቡ አይገባም፡፡ ልጃቸው አቶ ሀብተማርያም አመንቴ ከገብረ ጉራቻ አስተዳደር ጋር በመሆን በወቅቱ ውሉ እንዲፈርስ ጠይቆ ውሉ ሊፈርስ አይገባም ተብሎ በመዝገብ ቁጥር 36640 በቀን 03/08/2005ዓ.ም ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡ በወንጀል  ጥፋተኛ ናቸው ተብሏል  የተባለውንም በተመለከተ በወንጀል የተሰጠ የጥፋተኝነት ውሳኔ ለፍ/ብሄር ጉዳይ ሁልጊዜ በቂ ማስረጃ አይደለም፡፡ የቀረበው የቤቱ ግምት የተጋነነ ስለሆነ ተገቢ አይደለም በተጨማሪም ጥፋተኛ ሊባል የሚገባው ልጃቸው እንጂ እኛ አይደለንም በማለት መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ የካሳሾች ልጅ  የሆነው ሶስተኛ ተጠሪ ጣልቃ እንዲገባ የጠየቁ ሲሆን እሱም ጣልቃ በመግባት ተከሳሾች ጥፋተኛ በመሆናቸው ለደረሰው ጉዳት ካሳ ሊከፍሉ ይገባል በማለት መልሱን አቅርቧል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ምስክሮች እና የሰነድ ማስረጃዎች በመመርመር ለክርክር መነሻ በሆነው ቤት ላይ ከሳሾች መብት አላቸው ወይስ የላቸውም? ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት  ያለበት ማነው? የደረሰው

ጉዳት ምን ያህል ነው የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ የቀረቡት የከሳሾች ማስረጃዎች ከሳሾች ከንብረቱ መብት እንደሌላቸው ያረጋግጡ እንጂ ጣልቃ ገብ ግን ንብረቱ የከሳሾች መሆኑን የተከራከረ በመሆኑ ከሳሾች ከንብረቱ መብት አላቸው ተብሏል፡፡ ተከሳሾች በወንጀል የተከሰሱትና የተቀጡት የቤቱን ግምት በማሳነስና አንሶ የቀረበውን የንብረት ዋጋ በማረጋገጥ ነው፡፡ በፍ/ብ/ህ አንቀጽ 2149 በወንጀል ፍርድ ቤት በተሰጠው ፍርድ የፍ/ብሄር ፍርድ ቤት ካሳ ለመወሰን እንደማይገደድ ተደንግጓል እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 46386 እና 78479 አንድ ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ከተባለ ለፍ/ብሄር ጉዳይ ማስረጃው ቀርቦ መመዘን እንዳለበት እንጂ በወንጀል ጥፋተኛ ስለተባለ ብቻ ከሳ ክፈል ሊባል እንደማይችል አስገዳጅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ንብረቱም ለጣልቃ ገብ የዞረው በቁጥር 324/99 በቀን 30/09/1999 ዓ.ም በተጻፈ ውክልና በመሆኑ ለጉዳት ሊጠየቅ የሚገባው ጣልቃ ገብ እንጂ ተከሳሾች አይደሉም ጣልቃ ገብ 388,485,12 ብር ሊከፍል ይገባል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የአሁን ተጠሪዎች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 413473 ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን በማከራከር የስር ተከሳሾች በወንጀል ችሎት በቀረበባቸው የሰውና የሰነድ ማስረጃ ስልጣንን ያለአግባብ መገልገል ወንጀል መፈጸማቸው ተረጋግጦ ተቀጥተዋል፡፡ ለፍ/ብሄር ክርክር የሚቀርብ የማስረጃ ምዘና ከወንጀል የማስረጃ ምዘና የሚቀል ነው፡፡ የስር ተከሳሾች ጥፋተኛ መሆናቸው በተረጋገጠበት ሁኔታ የስር ፍርድ ቤት ተከሳሾች ካሳ ሊከፍሉ አይገባም ማለት በአግባቡ ባለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ተከሳሾችና ጣልቃ ገብ በጋራና በተናጠል ጥፋተኛ በመሆናቸው በስር ፍርድ ቤት የተወሰነውን 388,485.12 ብር ሊከፍሉ ይገባል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የአሁን አመልካቾች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም ፍርድ ቤቱም የቀረበውን አቤቱታ በመመርመር አያስቀርብም በማለት ሰርዞታል፡፡

የአሁን አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለዚህ ችሎት በቀን 14/03/2016ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ የሰበር አቤቱታቸውም ይዘት ከሳሾች ክርክር ያስነሳውን ቤት መሸጥና መለወጥ እንዲችል በቁጥር 324/99 በቀን 29/09/1999ዓ.ም በሰጡት ልዩ ውክልና ተጠቅሞ ቤቱን ወደ ራሱ ስም ዝውውር ያደረገው ልጃቸው መሆኑ ተረጋግጦ እያለ ከህግ ውጪ የፈጸምነው ተግባር በሌለበት ከአሁኑ 3ኛ ተጠሪ ጋር የጋራና የተናጠል ኃላፊነት አለባቸው ተብሎ የተሰጠብን ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፡፡ በወንጀል ተከሰን የተቀጣነው ውሉ አጽድቀን ስም ዝውውር በማድረጋችን ሳይሆን በወቅቱ የቤቱ ዋጋ ዝቅ ተደርጎ በመቅረቡ መንግስት ማግኘት የነበረበትን ገቢ አሳጥታችኋል በሚል ነው፡፡ ይህ ደግሞ ውጪ ከራስ ጋር የተደረገውን ውል ተቀብለን ስም ዝውውር በመፈጸማችን ጥፋተኛ አለመባላችን የሚያረጋግጥ ሆኖ እያለና እንደዛ ቢሆን እንኳን አንድ ሰው በወንጀል ተጠያቂ ስለተባለ ብቻ በፍትሃብሄር ጉዳይም የግድ ተጠያቂ መሆን ማለት እንዳልሆነና በወንጀል ጉዳይ የተሰማው ማስረጃ በተመሳሳይ በፍትሃብሄር ጉዳይም ተሰምቶ በተደረገ የማስረጃ ምዘና ጉዳይ የተረጋገጠ በሆነ ጊዜ ብቻ መሆኑን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ሰበር ችሎት በመ.ቁ46386 ቅጽ 13 ላይ ከፍ/ብ/ህ አንቀጽ 2149 ጋር በማያያዝ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ተሰጥቶ እያለ ይህንኑ ህግ ወደ ጎን በመተው የሰጡት መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው። በተጨማሪም ቤቱ በ2005 ዓ.ም በግልጽ ጨረታ ሲሸጥ 74,000 ብር ሆኖ እያለ ፍርድ ቤቱ 388,485.12 ብር እንድንከፍል መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊሻር እና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት አቤቱታቸውን አቅርበዋል።

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በማሻሻል አመልካቾች በተጠሪዎች ላይ የደረሰውን ጉዳት የመካስ የአንድነትና የነጠላ ኃላፊነት አለባቸው በማለት የደረሰበት መደምደሚያ እና ያሳለፈው ውሳኔ የግራ ቀኙን ክርክር እና በማስረጃ ተረጋገጠ የተባለውን ፍሬ ነገር መሰረት ያደረገ መሆን አለመሆኑን አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ጉዳዩ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 28(3) መሰረት ያስቀርባል በማለት ቅሬታው ለተጠሪዎች ደርሶ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በጠበቃቸው አማካኝነት በቀን 09/11/2016ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርበዋል። የመልሳቸውም ይዘት የወንጀሉም ሆነ የፍ/ብሄሩ ክርክር የክስ ምክንያት የተሰሙት ማስረጃዎች ድርጊቱን የፈፀሙት ግለሰቦች ተመሳሳይ በመሆናቸው በህገ ወጥ መንገድ ቤታችን ተሸጦ ለሌላ ሰው መተላለፉ የአመልካቾች ድርጊት ጥፋት ብቻ ሳይሆን ወንጀልም በመሆኑ ለደረሰብን ጉዳት ካሳ እንዲከፍሉ መባሉ በአግባቡ ነው። 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪ ባልና ሚስት መሆናችን እየታወቀ እንዲሁም የተሰጠው ልዩ ውክልና አይደለም እንጂ ልዩ ውክልና ነው ቢባል እንኳን የባልና የሚስት ፍቃድ መኖሩ መረጋገጥ ሲገባው ይህ ሳይሆን ስም መዞሩ በአግባቡ ባለመሆኑ ጥፋተኛ ናቸው። የቤቱ ግምትም ላይም ያቀረቡት አቤቱታ በአግባቡ ባለመሆኑ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት መልሳቸውን አቅርበዋል። 3ኛ ተጠሪ በበኩሉ በጠበቃቸው አማካኝነት በቀን 24/10/2016ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል በመልሱም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ በመሆኑ ሊፀና ይገባል ብሏል። አመልካቾችም የተጠሪዎች መልስ ደርሷቸው በቀን 26/11/2016ዓ.ም እና በቀን 09/11/2016ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር አቅርበዋል።

እኛም የቀረበውን ክርክር በክልል ፍርድ ቤቶች የተሰጠትን ውሳኔዎች እንዲሁም በመዝገቡ የተያዘውን ጭብጥ ከህግ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል። የፍ/ህ/ቁ2149 በወንጀል ክስ ተከሳሽ ነፃ መባሉ ወይም አያስከስሰውም ተብሎ መወሰኑ ከፍትሃብሄር ክስ ሊያድን እንደማይችል የሚደነግግ ነው። አመልካቾች በወንጀል አጥፊ የተባለ ስለሆነ ይህ ድንጋጌ በቀጥታ እነሱን ሊደግፍ የሚችል አደለም። በሰበር መዝገብ ቁጥር 46386 በተሰጠ ውሳኔ ደግሞ በወንጀል አጥፊ ሆኖ መገኘት ሁልጊዜም የፍትሃብሄር ሀላፊነት ያስከትላል ሊባል እንደማይችል ተወስኗል። ወደተያዘው ጉዳይ ስንመጣ የከሳሾች ልጅ የሆነው ሶስተኛ ተጠሪ ሀብተማርያም አመንቴ አንደኛ ተጠሪ ከሆኑት ከእናቱ በወሰደው ውክልና ላይ ተመስርቶ

በእናቱ ስም የሚታወቅ ቤት ወደራሱ በማዞር ከባንክ ብድር ከወሰደበት በኂላ የባንክ እዳ ባለመክፈሉ ቤቱን ባንክ ለእዳ መክፈያ እንደሸጠው መዝገቡ ያስገነዝባል፡፡

አመልካች በወንጀል ህ/ቁ407(1) አጥፊ ሆነው የተቀጡት ይህን ቤት የከሳሾች ልጅ ወደሆነው ሶስተኛ ተጠሪ በማዛወር ሂደት የመንግስት ስራ ሀላፊነታቸውን በአግባቡ ባለመወጣታቸው በስልጣን ያለአግባብ የመገልገል ወንጀል ፈጽመዋል ተብሎ ነው፡፡ በእርግጥ  በከሳሾች ላይ ለደረሰው ጉዳት የሶስተኛ ተጠሪና የአመልካቾች የጋራ አስተዋጽኦ አለው ሊባል ይችላል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የቤቱን ዋጋ በብድር መልክ ከባንክ ወስዶ ገንዘቡን የበላው  የከሳሾች ልጅ የሆነው 3ኛ ተጠሪ  ሀብተማርያም አመንቴ እንደሆነ መዝገቡ በግልጽ ያሳያል፡፡ ከዚህ ቤት ገንዘብ ውስጥ አመልካቾች ያገኙት ምንም ገንዘብ እንዳለ መዝገቡ አያሳይም፡፡ አንድ ሰው በወንጀል ህግ 407(1) አጥፊ ሲሆን  ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወንጀሉን ሊፈጽም ይችላል፡፡ ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመጣ አመልካቾች የከሳሾች ልጅ የሆነው 3ኛ ተጠሪ ሀብተማርያም አመንቴ እንዲጠቀም ከማረጋቸው ውጪ ለራሳቸው ምንም ጥቅም እንዳገኙ መዝገቡ አያሳይም፡፡

ጥቅሙ የገንዘብ ወይም የቁስ ጥቅም በሆነ ጊዜ የወንጀሉ ጥፋት በብዙ ሰዎች ንክኪ የተፈጸመ ቢሆንም ለተጎጂው ጉዳት ምክንያት የሆነውን የገንዘብ ጥቅም ያገኘው ማን መሆኑ በግልጽ  የታወቀ በሚሆንበት ጊዜ የበላውን ገንዘብ መመለስ የሚገባው ይህ ገንዘብ ወሳጅ ግለሰብ መሆን ይገባዋል፡፡ በዚህ ቤት ዋጋ ተጠቃሚ የሆነው የ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ልጅ እና  የ1ኛ ተጠሪ ተወካይ የሆነው ሀብተማርያም አመንቴ መሆኑን መዝገቡ በግልጽ ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል ይህ 3ኛ ተጠሪ የሆነው ሀብተማርያም አመንቴ እሱ በበላው ገንዘብ አመልካቾች ጭምር ለእናትና አባቱ የቤቱን ዋጋ መክፈል አለባቸው እያለ የሚከራከር ነው፡፡ ይህ ሁሉ የሚያሳየው ከሳሾች ልጃቸው የበላው መሆኑን በግልጽ በሚያቁት ገንዘብ ሌሎች ሰዎች እንዲከፍሉአቸው  የሚጠይቁ መሆኑንና ልጃቸው 3ኛ ተጠሪም እሱ የበላውን የናት አባቱን ገንዘብ ሌሎች ሰዎች እንዲከፍሉ በማለት የሚከራከር መሆኑን ነው፡፡ እንዲህ በግልጽ በታወቀ ነገር ደግሞ በወንጀል አጥፊ መሆን ሁል ጊዜም በፍትሄብሄር ባለእዳ ላያረግ የሚችልበት እድል ስላለ የፍትሃብሄር ተጠያቂ መሆን የሚገባው 3ኛ ተጠሪ ሀብተማርያም አመንቴ ብቻ ነው በማለት የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ በውጤት ደረጃ ተገቢ ነው ብለን ከዚህ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ውሳኔ**

- የኦሮሚያ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ436814 በጥቅምት 28/2016ዓ.ም የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ413473 በመስከረም 29/2016ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት  የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ሆኖ ስላላገኘነው በሰ/ስ/ስ/መ/ቁ17/2015 አንቀጽ 9(1)(ለ) መሰረት የሁለቱንም ችሎቶች ውሳኔ ሽረናል፡፡

ማስ ታወሻ፡ - ይህ የ ሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነ ድ ለ ጥና ትና ምር ምር ሥራ ወይምለ ግን ዛ ቤ እ ን ጂ ለ ፍር ድ አ ፈጻ ጸ ምዓ ላ ማ አ ያ ገ ለ ግልም!

- የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 97630 በግንቦት 8/2015 የሰጠውን ውሳኔ ተገቢ ሆኖ ስላገኘነው በሰ/ስ/ስ/መ/ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1)(ሀ) መሰረት በውጤቱ አጽንተነዋል፡፡
- በዚህ መዝገብ በታህሳስ 12/2016 የተሰጠውን እግድ አንስተናል፡፡ እግድ ለተላለፈላቸው ክፍሎች እግዱ መነሳቱ ይድረሳቸው፡፡
- የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 255190

ህዳር 26 ቀን 2017ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ብርቅነሽ እሱባለው

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች ፡- አቶ አየለ ሽፈራው - ቀረቡ

ተጠሪዎች ፡- 1. ጎባ ወረዳ ፍ/ቤት

2. ጎባ ወረዳ ፐብሊክ ሰርቪስ እና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የመንግሥት ሠራተኛን ከሥራና ከደመወዝ ማገድ ሕጋዊነትን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የደ/ም/ኢ/ት/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው በሥር ፍርድ ቤት አመልካች ይግባኝ ባይ ሲሆን ተጠሪዎች መልስ ሰጪዎች ነበሩ፡፡ ተጠሪ በ22/03/2015 ዓ/ም ለአስተዳደር ፍ/ቤት ጽፈው ባቀረቡት የይግባኝ ቅሬታ ተጠሪዎች የትምህርት ማስረጃዬ ሀሰተኛ ስለመሆኑ

ባላረጋገጡበት ዲፕሎማ ሰርተፍኬትህ ሀሰተኛ ነው በማለት ከስራ እና ደመወዝ ያለአግባብ ያገዱኝ ስለሆነ ወር ደመወዜ ከተቋረጠበት ከጥቅምት 1 ቀን 2015ዓ.ም ጀምሮ ተከፍሎኝ ወደ ሥራ እንድመለስ እንዲወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪዎች ባቀረቡት መልስ አመልካችን ከሥራና ከደመወዝ ለማገድ የበቁት በመንግስት በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት አመልካችን ጨምሮ የመንግሥት ሠራተኞች የትምህርት ማስረጃ ትክክለኝነት እንዲጣራ ተደርጎ የጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሥራ እና ክህሎት ቢሮ የትምህርት ማስረጃውን ሀሰተኛነት እና አመልካች ተምሬበታለሁ ያለውን ቡራይ ኮሌጅ ሁኔታ በማረጋገጥ የሰጠውን የማጣራት ውጤት መሠረት በማድረግ በመሆኑ እርምጃው ተገቢ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

የአስተዳደር ፍ/ቤቱም በመዝገብ ቁጥር0193/2015 ላይ የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ በሰጠው ውሳኔ የጋምቤላ ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሥራ እና ክህሎት ቢሮ አመልካች ተምረውበታል ያለውን ቡራይ ኮሌጅ ሁኔታና የትምህርት ማስረጃ ሀሰተኝነት በማረጋገጥ የሰጠውን የማጣራት ውጤት መሠረት በማድረግ የወሰዱት እርምጃ በመሆኑ አመልካችን ከሥራና ከደመወዝ ማገዱ የሚነቀፍ አይደለም በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍ/ቤቱ ግራቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኃላ ተጠሪዎች ለውሳኔያቸው መሰረት ያደረጉት የጋምቤላ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የሥራ እና ክህሎት ቢሮ በቁጥር ሥክ/313/15 ጥቅምት 21 ቀን 2015ዓ.ም የጻፈው ደብዳቤ አመልካች የተማረበት ቡራይ ኮሌጅ ምንም አይነት አገልግሎት እንዳይሰጥ ስለመታገዱ የሚገልጽ እንጂ የአመልካችን የትምህርት ማስረጃ ሀሰተኛነት የሚገልፅ ስላልሆነ የስር አስተዳደር ፍርድ ቤት አመልካች የተማረበት ቡራይ ኮሌጅ ከመቼ ጀምሮ እንደታገደ እና መቼ ክልሉን ለቆ እንደወጣ እንዲሁም የአመልካች ትምህርት ማስረጃ ሀሰተኛ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን በድጋሚ በማጣራት የመወሰለውን እንዲወስን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 343(1) መሠረት ወደ ሥር ፍ/ቤት በመመሪያ መልሶታል፡፡

2ኛ አመልካች በውሳኔው ቅር ተሰኝቶ የሰበር አቤቱታውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቦ ፍ/ቤቱ የግራቀኙን ክርክር ከመረመረ በኃላ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 186816 በሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሠረት የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 343(1) ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለሥር ፍ/ቤት ሲመልስ ማስረጃ ተጣርቶ እስከሚቀርብለት ድረስ የክርክሩን መዝገብ ለጊዜው የሚዘጋበት ሥርዓት እንጂ የሥር ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥ የሚያደርግ ሥርዓት አይደለም፡፡ ለአመልካች የትምህርት ማስረጃ ሰጥቷል የተባለው ቡራይ ኮሌጅ በክልሉ የታገደና ምንም ዓይነት አገልግሎት የማይሰጥና በክልላቸው የማይገኝ መሆኑን የጋምቤላ ክልል የሥራና ክህሎት ቢሮ ለ2ኛ ተጠሪ በገለጸው ማስረጃ መነሻ 2ኛ ተጠሪ በአመልካች ላይ የወሰደው እርምጃ አግባብ መሆኑን አረጋግጦ የአስተዳደር ፍ/ቤቱ ባጸናው ላይ እንደገና በድጋሚ እንዲጣራ በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ የሥነ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ሥርዓት ሕጉን ድንጋጌ ያላገናዘበና በተከራካሪ ወገኖች ላይ አላስፈላጊ ወጪና እንግልት የሚያስከትል ነው በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የአስተዳደር ፍ/ቤቱ የሰጠውን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ አመልካች በ14/03/2016 ዓ/ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን ይዘቱም፡- ቡራዩ ኮሌጅ አመልካች ተማሪዬ አይደለም ባላለበት እና አመልካች የተማሩት ኮሌጁ ከመታገዱ በፊት ወይም በኋላ መሆኑ ባልተረጋገጠበት ኮሌጁ በመታገዱ ብቻ የወሰዱት የትምህርት ማስረጃ ዋጋ እንዲያጣ ተደርጎ መወሰኑ አግባብ አይደለም፡፡  የጋምቤላ ስራና ክህሎት ቢሮ ጥቅምት 21 ቀን 2015ዓ.ም የጻፈው ደብዳቤ ኮሌጁ መታገዱን የሚገልጽ እንጂ መቼና ለምን እንደታገደ እንዲሁም ከክልሉ መቼ እንደወጣ የማያረጋግጥ በሆነበት የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም የሚል ነው፡፡

ሰበር ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 175/2011 አንቀጽ 80(5) መሰረት የአስተዳደር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በሰጡበት ጉዳይ ላይ የሚኖረው የይግባኝ ስልጣን የህግ ስህተትን ብቻ ማረም እንጂ የፍሬ ነገር ጉዳይን መርምሮ መወሰን አለመሆኑን መሰረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የስር አስተዳደር ፍርድ ቤት አከራካሪውን የትምህርት ማስረጃ ለአመልካች ሰጠ የተባለው የቡራይ ኮሌጅ ከመቼ ጀምሮ በጋምቤላ ክልል እንደታገደ፤እንዲሁም አመልካች የትምህርት ማስረጃ ሀሰተኛ ሊባል የሚችል ስለመሆን አለመሆኑ አጣርቶ እንዲወስን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 343(1) መሰረት በመመሪያ በመመለስ ያሳለፈው ውሳኔ ላይ የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 186816 የተሰጠውን ትርጉም እና የስነ ሥርዓት ህጉን ድንጋጌ ያላገናዘበ ነው በማለት መሻሩ የተጠቀሰውን የሰበር ውሳኔ እና የድንጋጌውን ትክክለኛ ይዘት እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የህግ ስህተት ብቻ ለማረም የተሰጠውን ስልጣን መሰረት ያደረገ መሆን አለመሆኑን አጣርቶ ለመወሰን የሚል ጭብጥ ተይዞ ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀርቡ አዟል፡፡

1ኛ ተጠሪ ሰኔ 6 ቀን 2016ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ የአመልካች አቤቱታ የፍሬ ነገር ክርክር በመሆኑ ሰበር ሰሚ ችሎቱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም፤ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10(1)(መ) መሠረት የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በክልል ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጡ ውሳኔዎችን ሊመለከት የሚችለው በአንቀጽ 2(4)ሀ-ሸ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ብቻ ስለሆነ አመልካች በየትኛው ምክንያት አቤቱታቸውን እንዳቀረቡ ያልገለጹ በመሆኑ በሰበር ሊታይ አይገባም፤ ከ2ኛ ተጠሪ በተጻፈልን ደብዳቤ መሠረት አመልካችን ያሰናበትን ስለሆነ ጉዳዩ 2ኛ ተጠሪን አይመለከትም የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማስቀደም አመልካች ተማርኩበት የሚሉት ኮሌጅ ያለው በጋምቤላ ሕዝቦ ክልል መንግስት ውስጥ ሲሆን የኮሌጁን እውቅናና ህጋዊነቱን ለማጣራት ለክልሉ ስራና ክህሎት ቢሮ ተጠይቆ ቢሮው በቁጥር ሲኪ/313/2015 በቀን 21/2/2015ዓ.ም በጻፈው ደብዳቤ ኮሌጁ ከጅምሩም የታገደና በክልሉ ውስጥ ምንም አገልግሎት የማይሰጥ ክልሉ ውስጥ የሌለ መሆኑን የተረጋገጠ በመሆኑ መቼ እና እንዴት የሚለውን ጥያቄ አያስነሳም፡፡አመልካች ቅሬታ ያቀረበው የዲፕሎማ ማስረጃውን የሚመለከት ብቻ ሲሆን

ለአመልካች ስንብት ምክንያት የሆነው ዲፕሎማው ብቻ ሳይሆን ከደረጃ ሁለት እስከ አራት ያለው የብቃት ማረጋገጫ ሀሰተኛ መሆን ጭምር በመሆኑ ያለብቃት ማረጋገጫ ዲፕሎማ ለብቻ የሚታይበት የትምህርት ስርዓት ስለሌለ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

2ኛ ተጠሪ በ06/10/2016 ዓ/ም ጽፎ ባቀረበው መልስ በአዋጅ ቁጥር 1234 አንቀጽ 2(4) መሰረት መስፈርትን አያሟላም፣ አመልካች ተማርኩ የሚሉበት ቡራይ ኮሌጅ ፍቃድ ከሚሰጠውና ከሚያስተዳድረው የክልሉ የስራና ክህሎት ቢሮ እውቅና ውጭ መሆኑ፤ምንም አይነት አገልግሎት የማይሰጥ እንዲሁም በክልሉ የማይገኝ መሆኑ በተረጋገጠበት እንዲሁም የአመልካች የብቃት ማረጋገጫ ሀሰተኛ መሆኑን የክልሉ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ አገልግሎት ቢሮ ያረጋገጠ በመሆኑ የስር ሰበር ሰሚ ችሎቱ የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው የሚል ነው፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የግራቀኙን ክርክር፣ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ እና ሕጉን መነሻ በማድረግ ውሳኔው ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች በ1ኛ ተጠሪ መሥሪያ ቤት ተቀጥረው ሲሰሩ ሀሰተኛ የትምሕርት ማስረጃ አቅርበዋል በሚል ከሥራና ከደመወዝ በመታገዳቸው አስተዳደራዊ ውሳኔውን በመቃወም ለአስተዳደር ፍርድ ቤት የቀረበ ይግባኝን መሠረት ተደርጎ የቀረበ ክርክር ነው፡፡ 1ኛ ተጠሪ አመልካች የሚሰሩበት መሥሪያ ቤት በመሆኑ በክርክሩ መሳተፉ ለክርክሩ አወሳሰንና ውጤት አስፈላጊ በመሆኑ በዚህ ረገድ በሰበር ክርክሩ ልሳተፍ አይገባም በማለት ያቀረበው ክርክር ተገቢነት የለውም፡፡

ክርክሩን በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሰረት መምራት እና መቆጣጠር የፍርድ ቤቱ ኃላፊነት ሲሆን በተገቢው ሁኔታ ካልተመራ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ዓላማዎች የሆኑትን እንደ አንጻራዊ እውነትን የመፈለግ፣ ሥነ-ሥርዓታዊ ፍትህ፣ ክርክርን ውጤታማ፣ ወጭና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ መምራት የመሳሰሉትን ማሳካት ስለማይቻል የተከራካሪዎችን መብት ይነካል፡፡ ክርክር የሚወሰነው በተጠየቀው ዳኝነት አግባብ እንደሆነ የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 182(2) ላይ ተመልክቷል፡፡ ፍርድ ቤቱም ከቀረበው ዳኝነት አኳያ ከግራቀኙ ክርክር በመነሳት በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 246 እና ተከታዮቹ መሠረት በተነሱት የሕግ ሆነ የፍሬ ነገር ጉዳዮች ጭብጥ የመመስረት፣ በክርክር የተነሱ ፍሬ ነገሮችን በማስረጃ አጣርተው የሕግ ውጤቱን የመወሰን ኃላፊነት አለባቸው፡፡

በክርክር ሂደት ፍሬ ነገሮችን ማረጋገጥ የሚቻልባቸው ዘዴዎች ማስረጃ፣ በፍርድ ቤት በሚሠጥ የእምነት ቃል፣ ፍርድ ቤት በራሱ ግንዛቤ ሊወስድባቸው የሚችሉ ጉዳዮች፣ የሕግ ግምት እና የመሓላ ቃል ናቸው፤በፍትሐ ብሔር ክርክር የምንከተለው የማስረዳት ደረጃ ከሁለቱ ወገን የተሻለ ያስረዳው ማን ነው የሚለውን በመመርመር ነው፤ የማስረጃ ተገቢነት፣ የማስረጃው ተቀባይነትን ደንቦችን መከተል እና

ለማስረጃው የሚሰጠውን ክብደት በመለየት የመወሰን ኃላፊነት ማስረጃ ለመስማትና ለመመዘን ኃላፊነት ያለባቸው ፍርድ ቤቶች ዋና ተግባር ነው።

በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 182(1) እንደተመለከተው በመጀመሪያ ደረጃ የሚሰጥ ፍርድ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን መነሻ ጉዳይ በአጭሩ የሚገልጽ መሆን አለበት የሚለው የቀረበውንም ማስረጃ ይዘት የሚመለከት ነው። ፍርድ በሚሰጥበት ጊዜም ምክንያትን ማስፈር እንደሚገባ በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ አንቀጽ 182(1) የተመለከተ ግዴታ ነው። ፍርድ በሚጻፍበት ጊዜ ስለጉዳዩ መግቢያ፣ በክርክሩ የተነሱትን ፍሬ ነገሮች ማስፈር፣ ምላሽ የሚያስፈልገውን የፍሬ ነገር ወይም የሕግ ጭብጥ መለየት፣ በተለየው ጭብጥ ማስረጃውን በመመዘን እና ተፈጻሚነት ያለውን ሕግ በመተግበር እና/ወይም በመተርጎም ለውሳኔው ምክንያትን በማስፈር ተፈጻሚ የሚሆነውን ዳኝነት የተጠቀበትን ጉዳይ እልባት መሥጠትን ይጠይቃል። በዚህም ተከራካሪ ወገን በአግባቡ የተሰማ፣ ማስረጃው በአግባቡ ግምት ውስጥ የገባና ዳኛው ሕጉን እና የቀረበውን ማስረጃ መሠረት አድርጎ የወሰነው ስለመሆኑ ሊያረጋግጥ የሚገባ ስለመሆኑ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 220801 ላይ ከሰጠው አስገዳጅ ትርጉም መገንዘብ ይቻላል።

በመንግሥት የሥራ ክርክር ከዳኝነት አካላት ፍሬ ነገር ሊያጣራ የሚችለው አስተዳደር ፍርድ ቤቱ ብቻ ነው፤ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 175/2011 አንቀጽ 80(5) መሰረት የአስተዳደር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በሰጡበት ጉዳይ ላይ የሚኖረው የይግባኝ ስልጣን የህግ ስህተትን ብቻ በማረም ላይ የተገደበ ነው። ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 186816 የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343(1) አስመልክቶ የሰጠው ትርጉም ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን የተሰጠውን ፍርድ ቤት የሚመለከት ነው። ማስረጃ ለመመዘን ሥልጣን ያልተሰጠው ፍርድ ቤት ፍሬ ነገሩ በሥር ፍርድ ቤት ተጣርቶና አባሪ ሆኖ እንዲቀርብለት ሊያዝና በኋላም ተጣርቶ ሲቀርብ ማስረጃውን መርምሮ ሊወሰን አይችልም። የሕግ ስህተት ብቻ እንዲመለከት ሥልጣን የተሰጠው ይግባኝ ሰሚ ችሎት የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343(1) ሥራ ላይ ሲያውል ጉዳዩ የተመለሰለት ፍርድ ቤት ማስረጃውን አጣርቶ እንደ አዲስ ውሳኔ የሚሰጥበት እንጂ ማስረጃውን አባሪ ሆኖ ጉዳዩ ለችሎቱ ሊመለስ አይችልም።

ስለሆነም የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያልተጣራ ፍሬ ነገር መኖሩን ሲገነዘብ ጉዳዩ በአስተዳደር ፍርድ ቤት ተጣርቶ እንዲወሰን መመለሱ በሕግ የተሰጠውን ሥልጣን መሠረት ያደረገ ሆኖ እያለ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎቱ ጉዳዩ የክርክር አመራር ግድፈት አለበት፣ የሰበር ሰሚ ችሎት መዝገብ ቁጥር 186816 የተከተለ አይደለም በማለት መሻሩ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው። ይግባኝ ሰሚ ችሎት ለአስተዳደራዊ ውሳኔ መሰረት የሆነው የጋምቤላ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የሥራ እና ክህሎት ቢሮ ጥቅምት 21 ቀን 2015ዓ.ም የጻፈው ደብዳቤ አመልካች የተማሩበት ቡራይ ኮሌጅ ምንም አይነት አገልግሎት እንዳይሰጥ ስለመታገዱ የሚገልጽ እንጂ የአመልካችን የትምህርት ማስረጃ ሀሰተኛነት የሚገልፅ ስላልሆነ የስር አስተዳደር ፍርድ ቤት አመልካች

የተማረበት ቡራይ ኮሌጅ ከመቼ ጀምሮ እንደታገደ እና መቼ ክልሉን ለቆ እንደወጣ እንዲሁም የአመልካች ትምህርት ማስረጃ ሀሰተኛ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን በድጋሚ በማጣራት የመወሰለውን እንዲወስን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 343(1) መሠረት ወደ አስተዳደር ፍርድ ቤቱ መመለሱ ጉዳዩን ለመወሰን አስፈላጊ የሆነው ፍሬ ነገር በተገቢው ማስረጃ ያልተጣራ መሆኑን በመረዳት ተገቢውን የክርክር አመራር ሥርዓት መሠረት ያደረገ ሆኖ እያለ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔውን መሻሩ የፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ያለውን አንጻራዊ እውነትን የመፈለግ ዓላማ እንዳይሳካ የሚያደርግና የአመልካችን የመደመጥ መብት የሚጥስ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 12643 ጥቅምት 14 ቀን 2016 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ 17/2015 አንቀጽ 9(1)(ለ) መሠረት ሽረናል፡፡

2. የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 14203 ሚያዚያ 18 ቀን 2015 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ 17/2015 አንቀጽ 9(1)(ሀ) መሠረት ፀንቷል፡፡

3. በዚህ ችሎት ግራቀኙ ያወጡት ወጭና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

- ውሳኔው ለሥር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- ውሳኔ ታህሳስ 09 ቀን 2017 ዓ/ም በችሎት ተነቧል፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 255586

ህዳር 26 ቀን 2017 ዓ/ም

ዳኞች ፡- እትመት አሰፋ

ደረጀ አያና

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

ብርሃኑ መንግሥቱ

አመልካች፡- ወ/ሮ የሺ ሽብሩ፡- ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ከበደ ድንቁ ፡- ከጠበቃ አለሙ ከልሌ ጋር ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ህዳር 25 ቀን 2016 ዓ.ም ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 431843 ህዳር 06 ቀን 2016 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 433385 ጥቅምት 14 ቀን 2016 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲታረምልኝ በሚል መነሻነት ነው፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ጉዳዩ የግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች የጋብቻ ፍቺን ተከትሎ በቀረበው የንብረት ክርክር ስምምነት ባልተደረሰባቸው ንብረቶች ላይ የቀረበ ዳኝነትን የሚመለከት ነው፡፡ክርክሩ ተጀመረው በሄጦሳ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች ከሳሽ ተጠሪ በሌላ በኩል ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡አመልካች ባቀረቡት ክስ የአመልካች እና ተጠሪ ጋብቻ ፍቺ ውሳኔን ተከትሎ በተደረገው የንብረት ክፍፍል መጋቢት 01 ቀን 2015 ዓ.ም ባደረግነው የዕርቅ ስምምነት የተወሰኑትን ንብረቶች የተከፋፈልን ሲሆን በስምምነት ያልተከፈልነው በምስራቅ መንገድ፣በምዕራብ ገመቹ ተሾመ፣በሰሜን ብርብርሳ ጅማ፣በደቡብ የሺ ጎሹ የሚዋስኑትን ባለ 60 ቆርቆሮ የመኖሪያ ቤት፣13 ሉክ ቆርቆሮ ኩሽና ቤት፣22 ቆርቆሮ የዕቃ ማጠራቀሚያ፣20 ሉክ ቆርቆሮ ቤተሰብ የሚገቡበት፣ ሶስት ሳር ቤት፣አንድ የከብቶች የሚገቡበት በረት ሌሎች ንብረቶችንም በዝርዝር በመጥቀስ ተጠሪ እንዲካፍለኝ የሚል ነው፡፡ተጠሪም በሰጡት መልስ የክርክር መነሻ የሆነው ንብረት በስምምነቱ ወቅት የእኔ እንደሆነ በተደረገው ዕርቅ ስምምነት የተደረሰበት በመሆኑ የቀረበው ክስ ውድቅ እንዲደረግ በሚል ተከራክረዋል፡፡

አቤቱታው የቀረበለት የወረዳ ፍርድ ቤትም የክርክር መነሻ የሆነው ይዞታ ግራ ቀኙ አብረው በሚኖሩበት ጊዜ በጋራ ያፈሩት ስለመሆኑ በችሎት ላይ የተደረገና ከዚህ በፊት የቀረበ የእርቅ ውጤት እንዲሁም ከገጠር የመሬት አስተዳደር ጽ/ቤት የቀረበ ማስረጃ የሚያስረዳ ነው በሚል እኩል እንዲካፈሉ የተወሰነ ሲሆን ተጠሪም በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆን ፍርድ ቤቱም በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም በሚል የቀረበውን አቤቱታ ሰርዞታል፡፡ተጠሪም በስር ፍርድ ቤቶች በተሰጠው ውሳኔ ባለመስማማት የይግባኝ አቤቱታቸውን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም በሰጠው ውሳኔ መጋቢት 01 ቀን 2015 ዓ.ም በተደረገው የዕርቅ ስምምነት መሠረት ሌሎች ንብረቶች እንደተጠበቁ ሆነው የክርክር መነሻ የሆነው የእርሻ መሬት የተጠሪ ሆኖ የተከፈለ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት መሬቱ የጋራ ንብረት ሆኖ ግራ ቀኙ እንዲካፈሉ በሚል የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም በሚል ውሳኔውን በማሻሻል ወስኗል፡፡አመልካችም የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲታረም በሚል ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታው ተቀባይነት አላገኘም፡፡

አመልካች በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ ሆነ ህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆኑን በመጥቀስ እንዲታረምልኝ በሚል ሐምሌ 18 ቀን 2016 ዓ.ም የተሻሻለውን የሰበር አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡በአመልካች የቀረበው ሰበር አቤቱታ ይዘትም በአጭሩ መጋቢት 01 ቀን 2015 ዓ.ም የተደረገው የዕርቅ ስምምነት የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ንብረት የጋራ ስለመሆኑ ስምምነት ላይ ያልተደረሰበት መሆኑን የሚያመለክት እንጂ የተጠሪ የግል ንብረት መሆኑን የሚያመለክት አይደለም፣የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ከዕርቅ ስምምነቱ ውጪ ንብረቱ የተጠሪ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

የግል ንብረት መሆኑ እንደተጠቀሰ በማድረግ የወረዳውን ፍ/ቤት ውሳኔ በማሻሻል የሰጠው ውሳኔ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ - መንግስት ንዑስ አንቀፅ 34 (1) እና 35 (7) እንዲሁም የተሻሻለውን የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 90 ድንጋጌዎችን የሚቃረን ስለሆነ እንዲታረምልኝ የሚል ነው፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም ለሰበር አቤቱታው ምክንያት የሆነው በምስራቅ መንገድ፤በምዕራብ አቶ ገመቹ ተሾመ፤በሰሜን ብርቢርሳ ጅማ እና በደቡብ የሺ ጎሹ የሚዋሰነው በሁለት ቀርጥ ይዞታ ላይ የሚገኙት ቤቶች እና ሌሎች ንብረቶች ግራ ቀኙ በአካባቢው ሽማግሌዎች አሸማጋይነት መጋቢት 01 ቀን 2015 ዓ.ም በተፈራረሙት የእርቅ ስምምነት መሰረት ለአሁን ተጠሪ እንዲሆን የተስማሙ በመሆኑ አመልካች ሊካፈሉ አይገባም በሚል በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔና ትዕዛዝ የተጠቀሰውን እርቅ ስምምነት ይዘት መሰረት ያደረገ መሆኑ እና ፍቺን ተከትሎ በሚኖር የጋራ ንብረት ክፍፍል ወቅት ሴቶች ያላቸውን ህገ-መንግስታዊ የእኩልነት መብት ያከበረ መሆኑ ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀፅ 34(1)፣ 35(7) አንፃር ለመመርምር ሲባል ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡

ተጠሪም በቀረበው የሰበር አቤቱታ ላይ ነሐሴ 20 ቀን 2016 ዓ.ም የተፃፈ መልስ ሰጥተዋል፡፡በተጠሪ የቀረበው መልስ ይዘትም በአጭሩ ከተጠሪ ጋር አስቀድሞ መጋቢት 01 ቀን 2015 ዓ.ም በተደረገው የዕርቅ ስምምነት መሠረት ንብረቶች ያሉበት መሬት የተጠሪ እንዲሆን እና ከላዩ ላይ የሚገኘውን ንብረቶች በተመለከተ ግን ልንግባባ ባለመቻላችን ጉዳዩ በሀገር ሽማግሌዎች አማካይነት የዕርቅ ስምምነት ተደርጎ በወረዳ ፍርድ ቤት የተመዘገበውን ስምምነት መሠረት ያደረገ እንጂ ከስምምነቱ ውጪ ለተጠሪ የተሰጠና የአመልካችንም የእኩልነት መብት የሚያሳጣ አይደለም፤አመልካችም በውሉ መሰረት ድርሻቸውን ወስደው በእጃቸው የሚገኝ ስለሆነ በድጋሚ ድርሻዬን የሚካፈሉበት አግባብ የሌለ በመሆኑ የቀረበው የሰበር አቤቱታ ውድቅ ተደርጎ በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ እንዲጸና በሚል ተከራክረዋል፡፡

አመልካችም ነሀሴ 28 ቀን 2016 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልሳቸውን በማቅረብ የሰበር አቤቱታቸውን አጠናክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለበትን ጭብጥ መሰረት በማድረግ የስር ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡እንደመረመርነውም ግራ ቀኙ የተከራካሪ ወገኖች ጋብቻ በፍቺ መፍረስን ተከትሎ መጋቢት 01 ቀን 2015 ዓ.ም ባደረጉት የዕርቅ ስምምነት ሌሎች በጋራ ያላቸውን ንብረቶች በስምምነት በመካፈል በስምምነት ላይ ሊደርሱ ያልቻሉትን አዋሳኞቹ በምስራቅ መንገድ፣ በምዕራብ ገመቹ ተሾመ፣በሰሜን ቢርቢርሳ ጅማ እንደዚሁም በደቡብ የሺ ጎሹ የሚዋሰኑትን ባለ 60 ሉክ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

ቆርቆሮ መኖሪያ ቤት፣13 ሉክ ቆርቆሮ ኩሽና፣22 ሉክ ቆርቆሮ የእህል ማጠራቀሚያ ቤት፣22 ሉክ ቆርቆሮ ቤተሰብ የሚኖርበት፣ሶስት የሳር ቤት እና አንድ ከብቶች የሚገቡበት በረት ስለመሆኑ ከዕርቅ ስምምነቱ ይዘት መረዳት የሚቻል ነው፡፡አመልካችም በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ተጠሪ በተጠቀሰው የዕርቅ ስምምነት መሰረት መስማማት ያልቻልነውን ንብረት እንዲያካፍለኝ በሚል መነሻነት ነው፡፡

ግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች ባልና ሚስት የነበሩ ሲሆን በመካከላቸው የነበረው ጋብቻ በፍቺ መፍረስን ተከትሎ ሎሎች የጋራ ንብረቶቻቸውን መጋቢት 01 ቀን 2015 ዓ.ም ባደረጉት የዕርቅ ስምምነት የተካፈሉ መሆኑንና መኖሪያ ቤትን ጨምሮ በተወሰኑት ንብረቶች ላይ ያልተስማሙበት ስለመሆኑ ከዕርቅ የስምምነቱ ይዘት የሚያስረዳ ሲሆን ተጠሪ በተደረገው የዕርቅ ስምምነት መሰረት አመልካች እንዲያካፍሏቸው ያቀረቡትን ንብረቶችን ተስማምተን ተካፍለናል የሚል ሳይሆን መሬቱ ለኔ የተከፈለ ነው የሚል ነው፡፡የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ለመሻር መነሻ ያደረገው የዕርቅ ስምምነቱን ሲሆን አመልካች ንብረቶቹን በእርቅ ስምምነት ተካፍለው እያለ ለተጠሪ የተካፈለውን መሬት ዳግመኛ የሚካፈሉበት አግባብ የለም በሚል ነው፡፡የግራ ቀኙ የዕርቅ ስምምነት በግልጽ እንደሚያስረዳው ተካራካሪዎቹ ወገኖች ሌሎች የጋራ ንብረቶቻቸውን በስምምነቱ መሠረት የተካፈሉ መሆናቸውንና በስምምነት ላይ ሊደርሱ ያልቻሉትን አዋሳኞቹ በምስራቅ መንገድ፣በምዕራብ ገመቹ ተሾመ፣በሰሜን ቢርቢርሳ ጅማ እንደዚሁም በደቡብ የሺ ጎሹ የሚዋሰኑትን ባለ 60 ሉክ ቆርቆሮ መኖሪያ ቤት፣13 ሉክ ቆርቆሮ ኩሽና፣22 ሉክ ቆርቆሮ የእህል ማጠራቀሚያ ቤት፣22 ሉክ ቆርቆሮ ቤተሰብ የሚኖርበት፣ሶስት የሳር ቤት እና አንድ ከብቶች የሚገቡበትን በረት መሆናቸውን የሚያሳይ እንጂ በተጠቀሰው አዋሳኝ ውስጥ የሚገኘው ንብረት ያረፈበት ይዞታ በክፍፍል ለተጠሪ የደረሳቸው በመሆኑ አመልካች ሊካፈሉ አይገባም የሚያስብል አይደለም፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 34(1) ላይ በጋብቻ ፍቺ ጊዜ ባልና ሚስት እኩል መብት ያላቸው ስለመሆኑና በአንቀጽ 35(7) ላይ መሬትን በመቆጣጠር ረገድ ሴቶች ከወንዶች እኩል መብት ያላቸው ስለመሆኑ የተደነገገ ሲሆን የተሻሻለው የኦሮሚያ ቤተሰብ ህግም በተመሳሳይ መልኩ አዋጅ ቁጥር 83/96 አንቀጽ 78 (1) ስር ባልና ሚስት ከግል ጥረታቸውና ከግል ወይም ከጋራ ንብረታቸው የሚያገኟቸው ገቢዎች እና ውጤቶች ሁሉ የጋራ ሀብቶቻቸው እንዲሚሆኑና የትዳር በፍቺ መፍረስን ተከትሎም የጋራ ሀብታቸው እኩል እንደሚከፋፈሉ የክልሉ ቤተሰብ ህግ አንቀጽ 117 እና ተከታዩቹ ስር ተዳንግጎ የሚገኝ ሲሆን ተከራካሪ ወገኖች የክርክር መነሻ የሆኑ ንብረቶች የሚገኙበትን አዋሳኝ በመጥቀስ መጋቢት 07 ቀን 2015 ዓ.ም በተደረገው የእርቅ ስምምነት መሠረት ግራ ቀኙ ሊከፋፈል የሚችልበትን አግባብ ያልተስማሙበት ሆኖ ንብረቶቹም በትዳር ውስጥ የተፈራ የጋራ ሀብት ስለመሆኑ ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች ተረጋግጦ በጋራ እንዲካፈሉ የተወሰነበት በአግባቡ ሆኖ እያለ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ድርሻቸውን ተካፍለዋል በሚል በወረዳው ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ

በመሻር ይዞታውን ከንብረቶቹ በመለየት የተጠሪ የግል ይዞታ ነው በሚል የተወሰነበት አግባባነት በህገ መንግስቱንና በቤተሰብ ህጉ መሠረት ሴቶች በጋብቻ እና በፍቺ ጊዜ ሊከበርላቸው የሚገባውን የእኩልነት መብት ያላገናዘበ ነው፡፡

ሲጠቃለል አመልካች እና ተጠሪ የክርክር መነሻ የሆነውና የጋራ ንብረታቸው የሆነውን አዋሳኞቹ በምስራቅ መንገድ፣ በምዕራብ ገመቹ ተሾመ፣በሰሜን ቢርቢርሳ ጅማ እንደዚሁም በደቡብ የሺ ጎሹ የሚዋሰኑትን ባለ 60 ሉክ ቆርቆሮ መኖሪያ ቤት፣13 ሉክ ቆርቆሮ ኩሽና፣22 ሉክ ቆርቆሮ የእህል ማጠራቀሚያ ቤት፣22 ሉክ ቆርቆሮ ቤተሰብ የሚኖርበት፣ሶስት የሳር ቤት እና አንድ ከብቶች የሚገቡበትን በረት የሚገኝበት ይዞታ የተጠሪ ነው በሚል የተወሰነበት አግባብ ከአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4)(ሀ) እና 10(1)(ሐ) መሠረት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡

በመሆኑም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ውሳኔ

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.431843 ህዳር 06 ቀን 2016 ዓ.ም በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 433385 ጥቅምት 14 ቀን 2016 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት የተሰጠው ውሳኔ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስነ ስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9(1)(ለ) መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 130535 ግንቦት 23 ቀን 2015 ዓ.ም እንደዚሁም የሂጦሳ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 36651 ሚያዝያ 13 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስነ ስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9(1)(ሀ) መሰረት ጸንተዋል፡፡
3. ግራ ቀኙ በሰበር ክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

ጉዳዩ ውሳኔ ስላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 255892

ህዳር 30ቀን 2017ዓ/ም

ዳኞች፡ ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ብርቅነሽ እሱባለው

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች፡ ዲቢኤል ኢንዳስትሪስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር - ጠበቃ ኤርሚያ አያሌው ቀረቡ

ተጠሪዎች፡ 1ኛ. አቶ ኣረጋዊ ስዩም

2ኛ. ወ/ት ትእግስቲ ተስፋይ

3ኛ. ወ/ት ትርሓስ አባዲ

4ኛ. አቶ ሳሙኤል በቀለ

5ኛ. አቶ አረጋ ካሳ

6ኛ. ወ/ት ሰላም አለማዮ

7ኛ. አቶ ኢሳያስ ኣምባሳጅር

8ኛ. አቶ የማነ ኣርአያ

9ኛ. አቶ መርሃዊ በሪሁ

10ኛ. ወ/ሪት ዋህድ ተኽሉ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ የቀረበው አመልካች በትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የመቐለ ዞን ፍርድቤት የኲሓ ክፍለከተማ ፍርድቤት በመዝገብ ቁጥር 85/2015 4879 በ30/12/2015ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ፤ የመቐለ ከተማ ከፍተኛ ፍርድቤት በመዝገብ ቁጥር በ03/2016/230

ማስታወሻ፡ - ይህ የ ሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነ ድ ለ ጥና ትና ምርምር ሥራ ወይምለ ግን ዛ ቤ እ ን ጂ

ለ ፍር ድ አ ፈጻ ጸ ምዓ ላ ማ አ ያ ገ ለ ግል ም!

በ25/1/2016ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ እንዲሁም የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 2016510 በ16/2/2016ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ ቅር በመሰኘት በ1/4/2016ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ስላቀረበ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ተጠሪዎች በትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የመቐለ ዞን ፍርድቤት የኵሓ ክፍለከተማ ፍርድቤት በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ በአመልካች ድርጅት ተቀጥረን 1ኛ ተጠሪ የወር ደመወዝ ብር 5750 እየተከፈለኝ በፕሮዳክሽን ቲም ሊደር የስራ መደብ፤ 2ኛ ተጠሪ የወር ደመወዝ ብር 7000 እየተከፈለኝ በጥገና የስራ መደብ፤ 3ኛ ተጠሪ የወር ደመወዝ ብር 6500 እየተከፈለኝ በፕሮዳክሽን የስራ መደብ፤ 4ኛ ተጠሪ የወር ደመወዝ ብር 6900 እየተከፈለኝ በኳሊቲ የስራ መደብ፤፤ 5ኛ ተጠሪ የወር ደመወዝ ብር 7000 እየተከፈለኝ በወርክ ስተዲ የስራ መደብ፤ 6ኛ ተጠሪ የወር ደመወዝ ብር 2500 እየተከፈለኝ በኳሊቲ የስራ መደብ፤ 7ኛ ተጠሪ የወር ደመወዝ ብር 6700 እየተከፈለኝ በከቲንግ የስራ መደብ፤ 8ኛ ተጠሪ የወር ብር 7000 እየተከፈለኝ በካድ የስራ መደብ፤ 9ኛ ተጠሪ የወር ደመወዝ ብር 7000 እየተከፈለኝ በፕሮዳክሽን የስራ መደብ፤ 10ኛ ተጠሪ የወር ደመወዝ ብር 6000 እየተከፈለኝ በፕሮዳክሽን የስራ መደብ ስንሰራ ቆይተን በትግራይ ክልል ባጋጠመ ጦርነት ምክንያት አመልካች ስራ ሊያቆም ችሏል፡፡

ከዚህ በኋላ አመልካች ስራዬን እያቆምኩኝ ስለሆነ ውል ስለማቋርጥ የሚገባችሁን ጥቅማ ጥቅም እንድሰጣችሁ ወኪል ወክላችሁ ወደ አዲስአበባ ላኩ ያለን ቢሆንም በነበረው ጦርነት ንግግሩ ቆሟል፡፡ ከፕሪቶሪያ ውል በኋላ ደግሞ አመልካች የሰራተኞች ደመወዝ እከፍላለሁ በሚል ምክንያት የድርጅቱን ንብረት በጨረታ ሸጦ ገቢ ሰብስቦ ውዝፍ ደመወዛችንን እንዲከፍለን ብንጠይቀውም ሊከፍለን አልቻለም፡፡ ስለሆነም አመልካች ከህዳር ወር 2013ዓ.ም እስከ ነሃሴ 2013ዓ.ም የ9 ወር ውዝፍ ደመወዝ የ1ኛ ተጠሪ ብር 51,750፤ የ2ኛ ተጠሪ ብር 63,000፤ የ3ኛ ተጠሪ ብር 58,500፤፤ የ4ኛ ተጠሪ ብር 62,100፤ የ5ኛ ተጠሪ ብር 63,000፤ የ6ኛ ተጠሪ ብር 22,500፤ የ7ኛ ተጠሪ ብር 60,300፤፤ የ8ኛ ተጠሪ ብር 63,000፤ የ9ኛ ተጠሪ ብር 63,000፤ የ10ኛ ተጠሪ ብር 54,000 በድምሩ ብር 561,150 እንዲከፍለን እንዲወሰንልን፤ የ2014ዓ.ም ሙሉ የ12 ወር ደመወዝ በድምሩ ብር 676,200 እንዲከፍለን፤ የ2015ዓ.ም ክስ እስከተመሰረተበት ቀን ድረስ የ8 ወር ደመወዝ ብር 498,000 አመልካች ከፍሎ ወደስራ እንዲመልሰን፤ ተጠሪዎች የ3 አመት ያልተጠቀምንበትን የአመት እረፍት ብር 87,999.99 ፤ ክፍያ ለዘገየበት የ3 ወር ደመወዝ በድምሩ ብር 204,750 በአጠቃላይ ብር 1,949,699.99 አመልካች እንዲከፍለን እንዲወሰንልን፡፡ የስራ ልምድ ማስረጃ፤ የስነምግባር ማስረጃ፤ ክሊራንስ፤ ከደመወዛችን ግብር እየተቆረጠ ስለመሆኑ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

የድጋፍ ደብዳቤ አመልካች እንዲሰጠን፣ አመልካች በ2013ዓ.ም የ9 ወር ደመወዝ እከፍላችኋለሁ በማለት የገባልንን የተስፋ ቃል እና በትግራይ ክልል ግዜያዊ መንግስት ክፊሏቸው ተብሎ መግባባት ላይ የተደረሰው የ3 ወር ደመወዝም እንዲከፍለን እንዲወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ማስረጃዎችንም አቅርበዋል፡፡

አመልካች ባቀረባቸው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች 1ኛ. ተጠሪዎች የጠየቁት የአመት እረፍት ክፍያ የመቼ፣ የማን የምን ያህል ቀን እንደሆነ በግልጽ ያላቀረቡ በመሆኑ ግልጽ አድርገው እንዲያቀርቡ ይህ ካልሆነ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ፣ 2ኛ. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድቤት ባወጣው አስተዳደራዊ ትእዛዝ መሰረት የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ በሚመለከት ክስ ባለበት ቆሞ እንዲቆይ የተደረገ በመሆኑ እና አመልካች በስራ ላይ ስለሌለሁና ገቢ ስለሌለኝ ክሱ እንዲቆም፣ 3ኛ. አመልካች ድርጅት የሚገኝበት የመቐለ ፍርድቤት ከመስከረም 7 ቀን 2014ዓ.ም ጀምሮ ስራ የጀመረ በመሆኑ ተጠሪዎች ከመስከረም 2014ዓ.ም ጀምረው በ6 ወር ግዜ ውስጥ ክሱን ባለማቅረባቸው በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 163(3) መሰረት ክሱ በይርጋ ቀሪ በመሆኑ ውድቅ እንዲደረግ በማለት ተከራክሯል፡፡

አመልካች ለፍሬጉዳዩ ባቀረበው መልስ አመልካች ለትርፍ አላማ ጨርቅ እያመረተ ወደ ውጭ ለመላክ የተቋቋመ ድርጅት ነው፡፡ አብዛኛውን ለምርት የሚገለገልበትን ግብአት የሚያገኘው እና የሚያቀርበው ከውጭ ሀገር ነው፡፡ በትግራይ ክልል በተፈጠረው ጦርነት ምክንያት የሚያሰራ ሁኔታ ስላልነበረ አመልካች ከ28/2/2013ዓ.ም ጀምሮ በይፋ ስላቆመ በስራ ላይ የለም፡፡ ተጠሪዎችን ጨምሮ ከ1800 በላይ ሰራተኞች ስራ ስላቆሙ እና ለደህንነታቸው ሲሉ ከጥቅምት 2013ዓ.ም ጀምረው ተበታትነው በስራ ላይ የሉም፡፡ በቀጠለው ጦርነትም በአመልካች እና በትግራይ ክልል ጥናትና ምርምር ባለሙያዎች ተጠንቶ አመልካች የ12,082,902 ዶላር ጉዳትና ውድመት ደርሶበታል፡፡ ይህ ከጥናቱ በኋላ የደረሰውን ጉዳት አይጨምርም፡፡ ይህን ጉዳት ለሚመለከታቸው የፌደራል እና የክልል አካላት ቀርቦላቸዋል፡፡ ከጥናቱ በኋላም ጸጥታው ዋስትና ስለሌለው ጉዳቱ እየቀጠለ ይገኛል፡፡

አመልካች ስራ ያቆመበት ምክንያት ዋነኛው ከአመልካች አቅም በላይ በሆነ ምክንያት ይኸውም ጦርነቱና ይህን ተከትሎ የኢትዮጵያ ሰራዊት ከህዳር እስከ ሚያዝያ 2013ዓ.ም ድርጅቱን ካምፕ አድርጎት ስለነበር፣ 103 የውጭ ሰራተኞች ከኢትዮጵያ ውጪ በመሄዳቸው አመልካች ከባድ የመሰረተ ልማት ውድመትና ዘረፋ ደርሶበታል፡፡ ምርት የሚቀበል ገዢ የግዢ ትእዛዙን በመሰረዙ

እና ግንኙነቱን በማቋረጡ፣ ከውጭ ተጭኖ እየመጣ የነበረ ግብአት ወደ ነበረበት እንዲመለስ በመደረጉ፣ ምርት ቢያመርትም ወደ ውጭ የሚልክበት እድል አለመኖሩ፣ ባንኮችም ዝግ ስለነበሩ ነው። ይህ ካጋጠመው በኋላ አመልካች ለትግራይ ክልል ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ በደብዳቤ እግዱን አሳውቋል። ቢሮው ውሳኔ ስላልሰጠ እንደተፈቀደ ነው የሚታሰበው። የእግዱ ግዜ ካበቃ በኋላ ደግሞ አመልካች ከሰራተኞቹ ጋር ያለው ውል እንዲቋረጥ ለቢሮው በደብዳቤ አሳውቆ መልስ አላገኘም። ስለሆነም ለሚመለከተው ለማሳወቅ አመልካች አስፈላጊውን ጥረት አድርጓል። በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 54(1) ድንጋጌ እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 20457(ቅጽ 4) እና 21329(ቅጽ 6) በሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ መሰረት ደመወዝ የሚከፈለው ለተሰራ ስራ ብቻ ነው። ስለሆነም አመልካች በበቂ ምክንያት ስራ ስላቆመ እና ተጠሪዎች ደግሞ ከጥቅምት ወር 2013ዓ.ም ጀምሮ እስካሁን በአመልካች ድርጅት ውስጥ ስላልሰሩ የጠየቁትን ደመወዝ የማግኘት መብት የላቸውም፣ አመልካችም የመክፈል ግዴታ የለበትም ተብሎ እንዲወሰን። የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት ውል በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1793(መ) መሰረት ጦርነት ከአቅም በላይ የሆነ ሀይል ስለመሆኑ በመደንገጉ አመልካች ለተጠሪዎች ደመወዝ ሊከፍል አይገባውም።

ተጠሪዎች ወደ ስራ እንድንመለስ በማለት የጠየቁትን በተመለከተ በጦርነቱ እና በደረሰው ከባድ ውድመትና አለመረጋጋት ምክንያት አመልካች አሁን የሚጀምርበት ሁኔታ የለም። አመልካች ለደረሰበት ጉዳት ካሳ ሳያገኝና ሳይጠገን አሁን አጋጥሞት ባለው ከባድ ችግር ወደ ስራ አይመለስም። ስለሆነም የተጠሪዎች ክስ ውድቅ እንዲደረግ። ተጠሪዎች አመልካች የሰራተኛን ደመወዝ ለመክፈል በኢንቨስትመንት ስም ከውጭ የተገዙ ንብረቶችን ሸጧል ያሉት ሀሰት ነው። ሸጧል ቢባል እንኳ አመልካች ስራ ባቆመበትና ተጠሪዎች ባልሰሩበት ደመወዝ የሚከፈልበት አግባብ የለም። አመልካች ለተጠሪዎች የገባሁት የተስፋ ቃል የለም። ከ1ኛ እና 8ኛ ተጠሪዎች በስተቀር ያሉት ተጠሪዎች የሚከፈላቸው ደመወዝ እነሱ እንዳሉት አይደለም። ተጠሪዎች የስራ ውላቸው የተቋረጠ ስለመሆኑ ያላስረዱ በመሆኑና፣ አመልካች ለተጠሪዎች የሚገባቸውን ክፍያ እንዲወስዱ ጥረት ሲያደርግ የነበረ በመሆኑ ክፍያ ለዘገየበት ልክፍል አይገባም። የአመት እረፍት ክፍያ ጥያቄን በተመለከተ የመቼ እና የማን ምን ያህል ነው? አመልካች ስራውን አቁሞ በነበረበት ግዜ ነው ወይንስ ከዛ በፊት ያለውን? የሚለውን ፍርድቤቱ እንዲያረጋግጥ እና ከጦርነቱ በፊት ያለውን ከሆነ ግን ተጠሪዎች በጠየቁት መሰረት ሳይሆን በማስረጃ ዝርዝር መግለጫቸው ላይ

ባቀረቡት ሰነድ መሰረት ያልተጠቀሙበትን የአመት እረፍት ህጉ በሚፈቅደው መሰረት ለመክፈል ፈቃደኛ ነኝ በማለት ተከራክሯል፡፡ ማስረጃዎችንም አቅርቧል፡፡

ፍርድቤቱም ክሱን የሰማ ሲሆን አመልካች በክስ መሰማት ሂደት ወቅት የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድቤት ባወጣው አስተዳደራዊ ትእዛዝ መሰረት የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ በሚመለከት ክስ ባለበት ቆሞ እንዲቆይ የተደረገ በመሆኑ እና አመልካች በስራ ላይ ስለሌለሁና ገቢ ስለሌለኝ ክሱ እንዲቆም በማለት ያቀረብኩት መቃወሚያ ይታለፍ በማለት በመግለጹ ይህ መቃወሚያው ታልፎ፣ የይርጋ መቃወሚያውን በ22/10/2015ዓ.ም በሰጠው ብይን ውድቅ አድርጎታል፡፡

በፍሬጉዳዩ ላይ ፍርድቤቱ ጭብጦችን በመያዝ የአመልካች እና የተጠሪዎችን ምስክሮች ከሰማ በኋላ ከሰነድ ማስረጃዎች ጋር መርምሮ ተጠሪዎች ከስራ እንደተሰናበቱ ያቀረቡት ክርክር ባለመኖሩ፣ አመልካችም ተጠሪዎችን ከስራ አሰናብቻለሁ ያላለ በመሆኑ፣ ለግዜው ስራ ያቆሙ ቢሆንም በመርህ ደረጃ አሁን ስራ ላይ እንዳሉ የሚታሰብ በመሆኑ ወደ ስራችን እንድንመለስ ይወሰንልን በማለት ዳኝነት የሚጠይቁበት አግባብ የለም በማለት ወስኗል፡፡ ተጠሪዎች ስራ ለመስራት ዝግጁ እንደነበሩ በአመልካች ችግር ምክንያት ግን መስራት እንዳልቻሉ ካቀረቡት ክርክርና ማስረጃ መገንዘብ የሚቻል ነው፡፡ በተጨማሪም አመልካች ከተጠሪዎች ጋር የነበረውን የስራ ውል እስካላቋረጠ ድረስ ተጠሪዎች በስራ ላይ እንዳሉ የሚገመት ነው፡፡ አመልካች በጦርነቱ ምክንያት ኪሳራና ውድመት እንደደረሰበት በምስክሮቹ ያስረዳ ቢሆንም ይህን ሊጠይቅ የሚገባው ለሚመለከተው አካል እንጂ የተጠሪዎችን ደመወዝ እንደ ማካካሻ ወይም መደራደሪያ የሚጠቀምበት የህግ ምክንያት የለም፡፡ ተጠሪዎች ባቀረቡት የእግድ ማመልከቻ ፍርድቤቱ ትእዛዝ ሲሰጥ በአመልካች ስም የሚታወቅ በተለያዩ ባንኮች በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ እንዳለ ተረጋግጧል፡፡ ይህም አመልካች ደመወዝ ለመክፈል አቅም እንዳለው የሚያስገነዝብ ነው፡፡ ተጠሪዎች አመልካች ሊከፍለን ቃል ገብቶልናል ያሉት የ9 ወር ደመወዝ እና በትግራይ ክልል ግዜያዊ መንግስት እንዲከፈላቸው የተባለው የ 3 ወር ደመወዝ በማለት የጠየቁት ዳኝነት በ29 ወራት ደመወዝ ውስጥ የተካተተ በመሆኑ ከዚህ አንጻር የዳኝነት ጥያቄያቸውን ውድቅ በማድረግ አመልካች ለተጠሪዎች ለእያንዳንዳቸው ከህዳር ወር 2013ዓ.ም ጀምሮ እስከ ግንቦት ወር 2015ዓ.ም ድረስ ያልከፈላቸውን ደመወዝ ለ1ኛ ተጠሪ የተጣራ የወር ደመወዝ ብር 4906 የ29 ወራት በድምሩ ብር 142,274፣ ለ2ኛ ተጠሪ የተጣራ የወር ደመወዝ ብር 5749 የ29 ወራት በድምሩ ብር 166,721፣ ለ3ኛ ተጠሪ የተጣራ የወር ደመወዝ ብር 3127 የ29 ወራት በድምሩ ብር 90,683፣ ለ4ኛ ተጠሪ የተጣራ የወር ደመወዝ ብር 5052.6 የ29 ወራት በድምሩ ብር 146,525.4፣ ለ5ኛ ተጠሪ የተጣራ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

የወር ደመወዝ ብር 2941 የ29 ወራት በድምሩ ብር 85,289፤ ለ6ኛ ተጠሪ የተጣራ የወር ደመወዝ ብር 2082 የ29 ወራት በድምሩ ብር 60,378፤ ለ7ኛ ተጠሪ የተጣራ የወር ደመወዝ ብር 5479 የ29 ወራት በድምሩ ብር 158,891፤ ለ8ኛ ተጠሪ የተጣራ የወር ደመወዝ የ29 ወራት በድምሩ ብር 199,288፤ ለ9ኛ ተጠሪ የተጣራ የወር ደመወዝ ብር 5464 የ29 ወራት በድምሩ ብር 158,456፤ ለ10ኛ ተጠሪ የተጣራ የወር ደመወዝ ብር 4940.5 የ29 ወራት በድምሩ ብር 143,274.5 እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡

የተጠሪዎችን የ3 አመት የአመት እረፍት ክፍያ ጥያቄ በተመለከተ አመልካች ስራ አቁሞ የነበረ በመሆኑ ተጠሪዎች የአመት እረፍት የሚጠይቁበት እድልና አመልካችም ፈቃድ የሚሰጥበት ሁኔታ ስላልነበረ አመልካች ለተጠሪዎች የአመት እረፍት መስጠት ይችል ነበር ወይንስ አይችልም? የሚለውን ማረጋገጥ አይቻልም፡፡ ይህ በሆነበት የአመት እረፍት ክፍያ ሊከፈል የሚገባው ጥያቄ ቀርቦ እረፍት ባለመወጣቱ በገንዘብ ታስቦ የሚከፈል በመሆኑ አመልካች የአመት እረፍት ተጠይቆ ወደ ሌላ ግዜ እንዲዞር ማድረጉ ስላልተረጋገጠ የአመት እረፍት ክፍያ ሊከፈል አይገባም በማለት ወስኗል፡፡ ተጠሪዎች የጠየቁት ደመወዝ እንዲከፈላቸው እንጂ  የስራ ውል እንዲቋረጥ የጠየቁት ዳኝነት ባለመኖሩ ከአዋጁ አንቀጽ 36 እና 38 ድንጋጌዎች አንጻር ክፍያ ለዘገየበት ሊከፈላቸው አይገባም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ተጠሪዎች ግብር እንደከፈሉ የሚገልጽ ማስረጃ ሊሰጣቸው ይገባል፤ ተጠሪዎች በስራ ላይ ስላሉና ከስራ ስላልተሰናበቱ ስነምግባርን የሚገልጽ ማስረጃ ወይም ክሊራንስ አመልካች ሊሰጣቸው አይገባም፤ ተጠሪዎች ስልጠና እንደወሰዱ የሚገልጽ ሰርተፍኬት ሊጠይቁ የሚገባው ስልጠናውን ከሰጠው አካል እንጂ አመልካች መስጠት የለበትም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች የስር ፍርድቤቱ የአመልካችን የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ በሰጠው ብይን እንዲሁም ፍሬጉዳዩን በተመለከተ አመልካች ለተጠሪዎች ለእያንዳንዳቸው የ29 ወራት ደመወዝ እንዲከፍላቸው በማለት በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለመቐለ ከተማ ከፍተኛ ፍርድቤት አቅርቦ ፍርድቤቱ በሰጠው ትእዛዝ ይግባኙን ሰርዞታል፡፡ በዚሁ ላይ አመልካች የሰበር አቤቱታ ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቦ ችሎቱም አቤቱታው ለሰበር ችሎት አያስቀርብም በማለት በሰጠው ትእዛዝ መዝገቡን ዘግቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የስር ፍርድቤቱ የአመልካችን የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ በሰጠው ብይን እንዲሁም ፍሬጉዳዩን በተመለከተ አመልካች ለተጠሪዎች ለእያንዳንዳቸው

የ29 ወራት ደመወዝ እንዲከፍላቸው በማለት በሰጠው ውሳኔ እና በዚሁ ብይን እና ውሳኔ ላይ የቀረበውን ይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ የክልሉ የበላይ ፍርድቤቶች በመሰረዝ የሰጡትን ትእዛዝ በመቃወም ሲሆን ይዘቱም የስር ፍርድቤት በአመልካች የቀረበውን የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ብይን የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድቤት ከሃምሌ 2014ዓ.ም ጀምሮ ፍርድቤቶች የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳዮችን ለማየት እንደሚችሉ ያወጣውን መመሪያ እና የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 163(3)ን ድንጋጌን የሚቃረን መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል፡፡

ፍሬጉዳዩን በተመለከተ ተጠሪዎች በስር ፍርድቤት ባቀረቡት ክስ እና በሰጡት ምስክርነት የአመልካች ፋብሪካ በትግራይ ክልል በተፈጠረው ጦርነት፤ የጸጥታ ችግር እና አለመረጋጋት ከ23/2/2013ዓ.ም ጀምሮ ስራ ማቆሙን ገልጸዋል፡፡ አመልካችም በመልሱ በክልሉ በተፈጠረው ጦርነትና ይህን ተከትሎ ባጋጠመው የፀጥታ እና የደህንነት ችግር እንዲሁም በፋብሪካው ላይ በደረሰው ከባድ ጉዳት እና ውድመት ምክንያት ስራ የሚሰራበት ሁኔታ ስላልነበረ ስራ መቆሙን እና ሰራተኞችንም ለደህንነታቸው ሲሉ መበተናቸውን እና ስራ ላይ እንዳልነበሩ፤ በተጨማሪም አመልካች በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ሆኖ የሰራተኞችን ውል እግድ እንዲሁም ስንብት በሚመለከት በተለያዩ ግዜያት ለክልሉ እና ለፌደራል የሰራተኛ ጉዳይ ቢሮዎች ያሳወቀ ቢሆንም ምላሽ ሳያገኝ መቅረቱን በሰነድ እና በምስክሮች አስረድቷል፡፡ የስር ፍርድቤቱ ይህን በፍርድ ሀተታው ላይ አስፍሮት ሳለ አመልካች የገጠመውን ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ከግምት ባለማስገባት ተጠሪዎች ለስራ ዝግጁ ሆነው በአመልካች ምክንያት ስራ እንዳልሰሩ በመግለጽ ጦርነቱ ከተጀመረበት ጀምሮ ተጠሪዎች ክስ እስከመሰረቱበት እለት ላሉት 29 ወራት ደመወዝ እንዲከፈላቸው በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡

አመልካች ከአቅሙ በላይ በሆነ ምክንያት ስራውን ባቆመበት ግዜ ይህም በተጠሪዎች በራሳቸው፤ በምስክሮች እና በሰነዶች ተረጋግጦ እያለ ለተጠሪዎች ስራ አለመስራት አመልካችን ተጠያቂ በማድረግ ተጠሪዎች ላልሰሩት ስራ ደመወዝ እንዲከፈላቸው የስር ፍርድቤት የሰጠው ውሳኔ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1791(2) እና 1793(መ) ድንጋጌዎችን የሚቃረን በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡ ከአሰሪው ቁጥጥር ውጪ በሆነ በተለይ ጦርነት በነበረበት እና ጦርነቱ ባስከተለው ጉዳት ሰራተኞች ወደስራ ቦታቸው ተገኝተው አገልግሎት ባልሰጡበት ሁኔታ ሰራተኞች ክፍያ የሚጠይቁበት እና አሰሪ እንዲከፍል የሚገደድበት የህግ መሰረት በሌለበት ሁኔታ የስር ፍርድቤት ለተጠሪዎች የ29 ወራት ደመወዝ እንዲከፈላቸው የሰጠው ውሳኔ የአሰሪና ሰራተኛ

ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 53 እና 54 ድንጋጌዎችን የሚቃረን መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድቤት አመልካች ለተጠሪዎች ለእያንዳንዳቸው የ29 ወራት ደመወዝ እንዲከፍል በማለት የሰጠው ውሳኔ እና የክልሉ የበላይ ፍርድቤቶች የሰጡት ትእዛዝ እንዲሻር የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ በሰበር ችሎቱ ተመርምሮ በግራቀኙ መካከል በነበረው ክርክር አመልካች ስራውን መቀጠል ያልቻለው በክልሉ በነበረ ጦርነት ምክንያት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ነው በማለት የሚያነሳው መከራከሪያ ውድቅ ተደርጎ ለተጠሪዎች ለእያንዳንዳቸው የ29 ወር ደመወዝ እንዲከፍል የስር ፍርድቤቶች የሰጡትን ውሳኔ አግባብነት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ተጠሪዎችን ያስቀርባል በማለት በ17/8/2016ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ መሰረት ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጓል፡፡

2ኛ፤ 4ኛ እና 10ኛ ተጠሪዎች በ30/11/2016ዓ.ም በተጻፈ ባቀረቡት መልስ የስር ፍርድቤቶች የሰጡት ውሳኔ እና ትእዛዝ አግባብ ነው የሚሉበትን ምክንያት በመግለጽ እንዲጸና፤ ወጪና ኪሳራ እንዲከፈላቸው እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡ 1ኛ ተጠሪ መጥሪያ ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆናቸው በመረጋገጡ፤ 3ኛ፤5ኛ፤ 6ኛ፤ 7ኛ፤8ኛ እና 9ኛ ተጠሪዎች መጥሪያ ደርሷቸው መልስ ባለማቀረባቸው ችሎቱ በ19/10/2016ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ መልስ የማቅረብ መብታቸውን አልፎታል፡፡ አመልካች 2ኛ፤ 4ኛ እና 10ኛ ተጠሪዎች ላቀረቡት መልስ በ13/12/2016ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ይህ የሰበር ሰሚ ችሎትም የአመልካችን ሰበር አቤቱታ አቤታ ከቀረበበት ውሳኔ በሰበር ችሎቱ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ እንዲሁም ከተገቢዎቹ የህግ ድንጋጌዎች አንጻር የስር ፍርድቤት አመልካች ለተጠሪዎች ለእያንዳንዳቸው የ29 ወራት ደመወዝ እንዲከፍላቸው በማለት የሰጠው ውሳኔ እና ይህም በክልሉ የበላይ ፍርድቤቶች ተቀባይነት ማግኘቱ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በኢፌዲሪ ህገመንግስት አንቀጽ 80(3)ም ሆነ በፌደራል ፍርድቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 ላይ በመጨረሻ ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ላይ እንጂ ማስረጃው ተመዝኖ የተደረሰበትን የፍሬነገር ድምዳሜ ላይ እንዲመለከት ስልጣን አልተሰጠውም፡፡ ነገር ግን ማስረጃ ለመመዘን ስልጣን የተሰጠው ፍርድቤት ማስረጃ ሲቀበል የተከራካሪዎችን እኩል የመደመጥ መብት ካላከበረ፤ የማስረዳት

ሸክም(burden of proof) የማን ነው የሚለውን ካልለየ፤ የማስረጃ ተቀባይነት እና ተገቢነት ላይ መከተል የሚገባውን ስርአት ካልተከተለ፤ በምዝና ግዜ ሁሉንም የተከራካሪዎች ማስረጃ አብሮ ካልመዘነ፤ የተለየ የማስረዳት ደረጃ(standard of proof) የሚጠይቁ ጉዳዮችን በሚጠይቀው ልክ መረጋገጡን ካላሳየ እና በመሰረታዊ ሕግም ሆነ በስነስርአት ህግ ያሉትን የማስረጃ ህጎችና መርሆዎች ካላከበረ ጉዳዩ የማስረጃ ምዘና ሳይሆን የህግ አተረጓጎም ስህተት እና ፍርድ ቤት ያለበትን ኃላፊነት አለመወጣት ስለሚሆን የሰበር ሰሚ ችሎቱ የሚመለከተው ጉዳይ እንደሆነ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 228614፤ 187971፤ 189534 እንዲሁም በሌሎች በርካታ መዛግብት አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

በግልጽ የቀረበን ክርክር በተቆጠረ ማስረጃ ወይም አግባብነት ባለው መንገድ እንዲጣራ(እንዲነጥር) ሳይደረግ የሚሰጥ ውሳኔ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 37105(ቅጽ 8) አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 52546(ቅጽ 12) አንድ ተከራካሪ ያቀረበውን ማስረጃ በግልጽ ምክንያቱ ተገልጾ ውድቅ ሳይደረግ፤ ሳይሰማ የታለፈበት ከሆነ የተከራካሪ ወገኖች የመሰማት መብት፤ የመከላከል መብት ብሎም በእኩልነት መርህ የመዳኘት መርህን የሚጥስ ነው በማለት አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 19 በአዋጁ አንቀጽ 18(5) ከ10 ተከታታይ ቀናት ላላነሰ ግዜ የድርጅቱን ስራ በሙሉም ሆነ በከፊል የሚያቋርጥ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ከስራ ውል የሚመነጩ መብትና ግዴታዎችን ለማገድ አሠሪው ለእገዳው ምክንያት የሆነው ሁኔታ ባጋጠመው በ3 የስራ ቀናት ውስጥ ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ላለው ባለስልጣን በጽሁፍ ማስታወቅ አለበት በማለት ደንግጓል፡፡ የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 20(1) ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያላው ባለስልጣን በአንቀጽ 19 የተጠቀሰው የጽሁፍ ማስታወቂያ በደረሰው በሶስት የስራ ቀናት ውስጥ ለእገዳው በቂ ምክንያት ስለመኖሩ ይወስናል፡፡ ሆኖም ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለስልጣን በሶስት የስራ ቀናት ውስጥ ውሳኔውን ካላሳወቀ እግዱን እንደፈቀደ ይቆጠራል በማለት ደንግጓል፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች በስር ፍርድቤት በተጠሪዎች ለቀረበለት የ29 ወራት ደመወዝ ይከፈለን ክስ ባቀረበው መልስ አመልካች በወቅቱ በትግራይ ክልል በተፈጠረው ጦርነት ምክንያት የሚያሰራ ሁኔታ ያልነበረ መሆኑን፤ አመልካች ስራ ያቆመበት ምክንያት ዋነኛው ከአመልካች አቅም በላይ

በሆነ ምክንያት ይኅውም ጦርነቱና ይህን ተከትሎ የኢትዮጵያ ሰራዊት ከህዳር እስከ ሚያዝያ 2013ዓ.ም ድርጅቱን ካምፕ አድርጎት ስለነበር፣ 103 የውጭ ሰራተኞች ከኢትዮጵያ ውጪ በመሄዳቸው አመልካች ከባድ የመሰረተ ልማት ውድመትና ዘረፋ የደረሰበት መሆኑን፣ ምርት የሚቀበል ገዢ የግዢ ትእዛዙን በመሰረዙ እና ግንኙነቱን በማቋረጡ፣ ከውጭ ተጭኖ እየመጣ የነበረ ግብአት ወደ ነበረበት እንዲመለስ በመደረጉ፣ ምርት ቢያመርትም ወደ ውጭ የሚልክበት እድል አለመኖሩ፣ ባንኮችም ዝግ ስለነበሩ መሆኑን በመግለፅ ይህ ካጋጠመው በኋላ አመልካች ለትግራይ ክልል ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ በደብዳቤ እግዱን ማሳወቁን ሆኖም ቢሮው ውሳኔ ስላልሰጠ እንደተፈቀደ ነው የሚታሰብ መሆኑን በመግለጽ፣ የእግዱ ግዜ ካበቃ በኋላ ደግሞ አመልካች ከሰራተኞቹ ጋር ያለው ውል እንዲቋረጥ ለቢሮው በደብዳቤ አሳውቆ መልስ አላገኘም በማለት መከራከሩን ከዚህ አንጻር ተጠሪዎች ስራ ስላልሰሩ ደመወዝ የማግኘት መብት የላቸውም በማለት መከራከሩን ከስር ፍርድቤት ውሳኔ ይዘት የምንገነዘበው ነው፡፡ ከዚሁ ክርክሩ ጋር በተያያዘም አመልካች በስር ፍርድቤት አመልካች ሰራተኞቹ ታግደው እንዲቆዩ ወደ ትግራይ ክልል ሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ በ25/5/2013ዓ.ም የጻፈውን ደብዳቤ በማስረጃነት ያቀረበ ስለመሆኑ ከስር ክርክሩ ይዘት የምንገነዘበው ነው፡፡ ይህ ሆኖ ሳለ ማስረጃን የመስማት የመመርመር እና የመመዘን በህግ ስልጣን የተሰጠው የስር ፍርድቤቱ በዚሁ መልኩ ከቀረበው የአመልካች ክርክር እና ማስረጃ አንጻር ጉዳዩን በአግባቡ ሊያጣራ፣ ሊመረምር እና ማስረጃውንም ከሌሎቹ ማስረጃዎች ጋር በመመርመር እና በመመዘን ውሳኔ ሊሰጥበት ሲገባ ይህን ሳይፈጽም፣ የማስረጃ ምዘናን መሰረታዊ መርሆዎችን ጭምር በመጣስ፣ በቀረበው ክርክር እና ማስረጃ ላይ ምንም ሳይል በማለፍ አመልካች ለተጠሪዎች ከላይ በተዘረዘረው መልኩ ለእያንዳንዳቸው ከህዳር ወር 2013ዓ.ም ጀምሮ እስከ ግንቦት ወር 2015ዓ.ም ድረስ ያለውን የ29 ወራት ደመወዝ እንዲከፍላቸው በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍል፣ በዚሁ የውሳኔ ክፍል ላይ የቀረበውን ይግባኝ የመቐለ ከተማ ከፍተኛ ፍርድቤት በመሰረዝ የሰጠው ትእዛዝ እንዲሁም በዚሁ ላይ የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታው ለሰበር ችሎት አያስቀርብም በማለት የሰጠው ትእዛዝ ይህ ችሎት ሊታረም የሚገባው መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝቶታል፡፡ ስለሆነም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. በትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የመቐለ ዞን ፍርድቤት የኵሓ ክፍለከተማ ፍርድቤት በመዝገብ ቁጥር 85/2015 4879 በ30/12/2015ዓ.ም ከላይ በፍርዱ ክፍል በተዘረዘረው

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

መልኩ አመልካች ለተጠሪዎች ለእያንዳንዳቸው ከህዳር ወር 2013ዓ.ም ጀምሮ እስከ ግንቦት ወር 2015ዓ.ም ድረስ ያለውን የ29 ወራት ደመወዝ እንዲከፍላቸው በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍል እና በዚሁ የውሳኔ ክፍል ላይ የቀረበውን ይግባኝ የመቐለ ከተማ ከፍተኛ ፍርድቤት በመዝገብ ቁጥር በ03/2016/230 በ25/1/2016ዓ.ም በመሰረዝ የሰጠው ትእዛዝ እንዲሁም በዚሁ ላይ የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 2016510 በ16/2/2016ዓ.ም አቤቱታው ለሰበር ችሎት አያስቀርብም በማለት የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽረዋል፡፡

2. ከላይ በውሳኔው ክፍል ተራ ቁጥር 1 ላይ ከተገለጸው ነጥብ ውጪ በትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የመቐለ ዞን ፍርድቤት የኵሓ ክፍለከተማ ፍርድቤት በመዝገብ ቁጥር 85/2015 4879 በ22/10/2015ዓ.ም የሰጠው ብይን እና በ30/12/2015ዓ.ም በሌሎች ጉዳዮች ላይ የሰጠው የውሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡
3. በትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የመቐለ ዞን ፍርድቤት የኵሓ ክፍለከተማ ፍርድቤት የመዝገብ ቁጥር 85/2015 4879 የሆነውን መዝገብ አንቀሳቅሶ አመልካች ከላይ በፍርድ ሀተታው ላይ በተገለጸው መልኩ በወቅቱ በትግራይ ክልል ከነበረው ጦርነት አንጻር ስላጋጠመው ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት በዝርዝር ያቀረበውን ክርክር እና ከዚሁ ክርክሩ ጋር አያይዞ በማስረጃነት ያቀረበውን አመልካች ሰራተኞቹ ታግደው እንዲቆዩ ወደ ትግራይ ክልል ሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ በ25/5/2013ዓ.ም የጻፈውን ደብዳቤ ከቀረቡት ሌሎቹ የአመልካች እና የተጠሪዎች ማስረጃዎች ጋር በመመርመር እና በመመዘን ጉዳዩን አጣርቶ ተጠሪዎች አመልካች ለእያንዳንዳችን ከህዳር ወር 2013ዓ.ም ጀምሮ እስከ ግንቦት ወር 2015ዓ.ም ድረስ ያለውን የ29 ወራት ደመወዝ እንዲከፍለን እንዲወሰንልን በማለት ባቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ላይ ተገቢ ነው የሚለውን ውሳኔ ሊሰጥ ይገባል በማለት ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 343(1) መሰረት መልሰንለታል፡፡
4. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍርድቤቶች ይድረስ፡፡
5. መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነ ድ ለ ጥና ትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

**የሰ/መ/ቁ** 256224

**ህዳር 30ቀን 2017ዓ/ም**

ዳኞች፡-ሽመክት አሰፋ

እንዳሻው አዳነ

አለማየሁ ሹናራ

ተናኜ ጥላሁን

ዋዚሞ ዋሲራ

**አመልካች፡-** አቶ እሸቱ መንጋው ቀርበዋል

**ተጠሪ፡-** 1. አቶ መሀመድ ሀብታሙ

2. ወ/ሮ ድርቧ ወዳይነው

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍርድ**

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ታህሳስ 9 ቀን 2016 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ የላስታ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 0114953 ግንቦት 04 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠውንና የሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 40112 ሰኔ 14 ቀን 2015 ዓ.ም የጸናውን ውሳኔ የአ.ብ.ክ.መ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ 0339501 በሕዳር 21 ቀን 2016 በመሻሩ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው በማቅረባቸው ነው፡፡


ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ጉዳዩ የቤት ሽያጭ ውልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በላስታ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪዎች ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል፡፡

አመልካች ያቀረቡት ክስ ይዘት በላሊበላ ከተማ ደ/ዘይት ቀበሌ የሚገኘውን ካርታና ፕላን ያለውን ይዞታ በቀን 20/10/2014 ዓ.ም በተደረገ ውል በብር 550,000 የሸጡልኝ እና 400,000 ብር ክፍያ ፈፅሜ ቀሪውን ብር 150,000 ስከፍል ስም እንዲያዛውሩልኝ ስጠይቃቸው ፍቃደኛ ያልሆኑ በመሆኑ ቀሪውን ገንዘብ ከፍዬ የቤቱን ስም እንዲያዛውሩልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና አማራጭ መልስ ያቀረቡ ሲሆን የመልሳቸውም ይዘት በአመልካችና በተጠሪ መካከል የፀና ውል የለም፣ አለ ከተባለ እንኳን አመልካች ቀሪ ክፍያውን ፈፅሞ ስም እንዳናዛውርለት ብንጠይቀውም በውሉ ላይ ከተጠቀሰው 8 ወራት ያዘገየና እንደ ውሉ ያልፈፀመ በመሆኑ እንደ ውሉ የምንፈፅምበት አግባብ የሌለ በመሆኑ የቀረበው ክስ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል ሕጋዊ የቤት ሽያጭ ውል አለ ወይስ የለም? አለ ከተባለ ውሉ ሊፈርስ ይገባል ወይስ አይገባም? ሊፈርስ አይገባም ከተባለ ከሳሽ ቀሪ ብር ክፍሎ ተከሳሽ ስመ ሀብት ዝውውር ሊያደርግ ይገባል ወይስ አይገባም የሚሉትን ጭብጦች በመያዝና የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን በመመርመር ተጠሪዎች ከአመልካች ጋር በህግ ፊት ሊፀና የሚችል በአዋዋይ አካል ፊት ያደረግነው ውል የለም ያሉ ሲሆን ከሳሽ ደግሞ ከተከሳሾች ጋር በቀን 20/10/2014 ዓ.ም በፅሁፍ ያደረጉትን የቤት ሽያጭ ውል አቅርበዋል፡፡ የጋራ ምስክሮች የሆኑት 1ኛ እና 2ኛ ምስክሮች ከሳሽና ተከሳሾች የቤት ሽያጭ ውል በብር 550,000 ሲያደርጉ እማኞች የነበሩና ከሳሽ ለተከሳሾች 400,000 ብር ከፍለው ቀሪ 150,000 ብር ያልከፈሉ መሆኑን መስክረዋል በመሆኑም በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል ህጋዊ የቤት ሽያጭ ውል አለ፤ በፍ/ብ/ህ/ቁ 2875 በፅሁፍ የተደረገ የቤት ሽያጭ ውል ያለና ከሳሽ 400,000 ብር ከፍለው ያልከፈሉት 150,000 ብር ያለ ሲሆን ይህንንም ቀሪ ክፍያ ለተከሳሾች ከፍለው ተከሳሾች ለከሳሽ ስመ ሀብቱን ሊያዛውሩ ይገባል እንጂ ውሉ የሚፈርስበት አግባብ የለም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በዚህም ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን በማከራከር የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አፅንቶታል፡፡

ተጠሪዎች ለአ.ብ.ክ.መ. ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር ቅሬታ ያቀረቡ ሲሆን ሰበር ሰሚ ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር በመመርመር የወረዳው ፍርድ ቤት የሽያጭ ውሉ ህጋዊ ነው በማለት ከሰጠው ምክንያት በተጨማሪ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 56794 በቅፅ 12 የሰጠውን ውሳኔ መሰረት በማድረግ ተጠሪዎች ከአመልካች ቀብድ የተቀበሉ በመሆኑ የቤት ሽያጭ ውል አለ ማለቱ በአግባቡ አይደለም ምክንያቱም ተጠሪዎች ከአመልካች ጋር ውል የሌላቸው መሆኑን የቀረበውም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

የሽያጭ ውል ረቂቅ ነው በማለት ክደው የተከራከሩና በውል አዋዋይ ፊት ያልተደረገ ቀብድ ስለተከፈለ ብቻ ህጋዊ ውል አለ የሚባልበት አግባብ የለም በማለት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ሽሯል፡፡

የሰበር ቅሬታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካች በታህሳስ 09 ቀን 2016 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡ ይዘቱም በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል በሰኔ 24 ቀን 2014 ዓ.ም ያደረጉት የቤትና የቦታ ሽያጭ ውል በግልፅ ያልተካደ በቃል ክርክር ወቅት ሙሉ ለሙሉ የታመነ ሆኖ ሳለ፣ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ አንቀፅ 235 ተከሳሽ የቀረበበትን ክስ በግልፅ ነገሩን በመካድ ምላሽ ካልሰጠ እንደታመነ የሚቆጠር በመሆኑና ተከሳሾች በቃል ክርክር ወቅት ከከሳሽ ጋር የቤትና የቦታ ሽያጭ ውል አለን ወይም አይካድም ባሉበት ሁኔታ በፅሁፍ በሰጡትም መልስ በግልፅ ከከሳሽ ጋር የቤትና የቦታ ሽያጭ ውል አላደረግንም በማስረጃነት የቀረበውን ውልም አናውቀውም በማለት ባልካዱበት ሁኔታ በተጨማሪም አከራካሪው ይዞታ የተገኘው በሊዝ ውል በመሆኑ በሊዝ ውል በተገኘ ይዞታ ግለሰቦች የሚያደርጉት የቤት ሽያጭ ውል ህገወጥ ነው የሚለው በስር ፍርድ ቤት ያልተነሳ ክርክርና አዲስ የቀረበ ክርክር ሆኖ እያለ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በአዋዋይ ፊት ያልተደረገ ውል ነው ተብሎ ፍርስ ማደረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ተሽሮ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡

የአመልካች አቤቱታ ከስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔዎችና ከተገቢው ሕግ ጋር አጣምሮ በመመርመር በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል ሰኔ 20 ቀን 2014 ዓ.ም በተደረገው የቤት ሽያጭ ውል በተመለከተ የስር ፍርድ ቤቶች በተጠሪ በህግ አግባብ የተደረገ ውል የለም በማለት ያቀረቡትን መከራከሪያ እና ማስረጃ በመስማት የሰጡትን ውሳኔ በሰበር የተመለከተው የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የፍ/ብ/ህ/ቁ 1723 በውል አዋዋይ ፊት አልተደረገም በማለት የሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ከሰ/መ/ቁ 36887፣ 21448፣ 211204 እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንፃር ለመመርመር የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

ተጠሪዎች መጋቢት 27 ቀን 2016 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት መልስ ይዘት በወረዳው ፍርድ ቤት ለቀረበው ክስ መልስ ስንሰጥ ከአመልካች ጋር ያደረግነው በህግ ፊት የሚፀና የቤት ሽያጭ ውል የለንም፣ የቀረበው ሰነድ ረቂቅ ነው በማለት የተከራከርን በመሆኑ እንደዚህ ብሎ የሚከራከር የቤት ሽያጭ ውል አለመፈፀሙን ክዶ እንደተከራከረ የሚቆጠር መሆኑን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰ/መ/ቁ 215762 አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠበት በመሆኑ፣ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 237 አማራጭ መልስ ማቅረብ የተፈቀደ በመሆኑ ከጅምሩ ውል የለም እንጂ ውል አለ የሚባል ከሆነ እንኳን በማለት ምላሽ መስጠታችን አመራጭ መልስ መስጠት እንጂ በግልፅ አለመካድ ነው የሚባልበት አግባብ የሌለ በመሆኑ፣ ውል አለ ቢባል እንኳን በሊዝ የተገኘ ይዞታን በሽያጭ ማስተላለፍ የሚከለክልና በዚህ ላይ የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 56252 በቅፅ 12 ውሳኔ የሰጠበት በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር

ውሳኔ መስጠቱ በአግባቡ ነው፡፡ በተጨማሪም ተጠሪዎች በስር የወረዳው ፍርድ ቤት ያቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ በቅድሚያ ምንም አይነት ብይን ሳይሰጥ በዝምታ ያለፈው መሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 174386 እና 59294 የሰጠውን አስገዳጅ ውሳኔ እንዲሁም በአማራጭ መልስ ባቀረብነው ክርክር ላይ ጭብጥ ያልተያዘ ማስረጃ ያልተሰማበት እና ውሳኔ ያልተሰጠበት መሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 39568 የሰጠውን አስገዳጅ ውሳኔ የወረዳው ፍርድ ቤት ያለፈው በመሆኑ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የክልሉን ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ሽሮ ውል አለ የሚል ከሆነ የስር የወረዳው ፍርድ ቤት በአማራጭ ክርክራችን ላይ ተገቢውን ጭብጥ ይዞ አከራክሮ እንዲወስን በነጥብ ሊመልስልን ይገባል በማለት መልሳቸውን አቅርበዋል፡

አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን የሚያጠናክር ሚያዚያ 16 ቀን 2016 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገቡ ጋር እንዲያያዝ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ፣ ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እና ቅሬታው ለሰበር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ነጥብ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደሚቻለው አመልካቸ በላስታ ወረዳ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ በመካከላቸው የቤት ሽያጭ ውል ያለ በመሆኑ ተጠሪዎች በውሉ መሰረት ቤቱን እንዲያስረክብ አመልካች ቀሪ ክፍያውን እንዲፈፅም የሚጠይቅ ሲሆን ተጠሪዎች የሰጡት መልስ በመካከላቸው የፀና ውል የሌለ መሆኑን እና አለ ከተባለ እንኳን አመልካች ቀሪ ክፍያውን ፈፅሞ ስም እንዳናዛውር ቢጠየቁም በውሉ ላይ ከተጠቀሰው ጊዜ ያዘገየ በመሆኑ እንደ ውሉ ለመፈጸም አንገደድም በማለት መልስ መስጠታቸው እና የስር ፍርድ ቤትም በመካከላቸው ህጋዊ የቤት ሽያጭ ውል አለ በማለት አመልካች ቀሪ ክፍያ እንዲፈጽሙ እና ተጠሪዎች ስመ ሀብቱን ሊያዛውሩ በማለት የወሰነና በይገባኝ ሰሚው የጸና ቢሆንም የክልሉ ሰበር ችሎት ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው አካል ፊት የተደረገ የቤት ሽያጭ ውል የለም በማለት መወሰኑን የሚመለከት ነው፡፡

በመሠረታዊነት ተዋዋይ ወገኖች በፈለጉት አይነት ፎርም እና ሁኔታ ዉል ቢዋዋሉ ዉላቸዉ የሕግ ደረጃ ተሰጥቶት የሚያስገድዳቸዉ ይሆናል፡፡ ሕግ በልዩ ሁኔታ አንድ ዉል መደረግ ስላለበት የአጻጻፍ ስርዓትና (ፎርምና) ምዝገባ በተመለከተ የደነገገዉ ካለ ይሄዉ የአጻጻፍ ስርአት(ፎርም) ተፈጻሚ መሆን ይኖርበታል፡፡ የአንድን ዉል ጉዳይ መሰረት በማድረግ ዉሉ ልዩ የአጻጻፍ ሥርዓት ተከትሎ እንዲደረግ በሕግ የተደነገገ እንደሆነ ተዋዋይ ወገኖች ዉላቸዉን በሕግ በተወሰነዉ ፎርም መሰረት የማድረግ ግዴታ እንዳለባቸዉ እና ይህን ካላደረጉ ዉሉ ሕጋዊ ዉጤት እንደማያስከትል በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1678፣1719 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ላይ የተመለከተዉ ያሳያል፡፡ ልዩ የአጻጻፍ ሥርዓትን ተከትለዉ እንዲደረጉ በሕግ ክተለዩት የዉል ጉዳዮች ዉስጥ አንዱ የማይንቀሳቀስ ንብረትን ባለቤትነት ለማስተላለፍ የሚደረግ ዉል

ነዉ፡፡ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1130 ስር እንደተደነገገዉ የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች የሚባሉት መሬትና ቤት ናቸዉ፡፡ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723/1 መሰረት የማይንቀሳሰቀስ ንብረት ባለቤትነትን በሽያጭ ለማስተላለፍ የሚደረግ የሽያጭ ዉል በጽሁፍ ሆኖ ዉል ለማዋዋል በሕግ ሥልጣን በተሰጠዉ አካል ፊት መደረግና መረጋገጥ(መመዝገብ) እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ ይህንን አጻጻፍ ተከትሎ ያልተደረገ የቤት ሽያጭ ዉል እንደረቂቅ እንደሚቆጠርና ሕጋዊ ዉጤት እንደማያስከትል ከፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1720/1 እና 1723/1/ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 21448 ላይ የሰጠዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉምም ይህንኑ የሚያሳይ ነዉ፡፡

በሌላ በኩል የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ዉል መደረጉን ግራ ቀኙ የተማመኑ እንደሆነ ወይም ተዋዋዮች የሽያጭ ዉል በመካከላቸዉ መኖሩን ያልተካካዱ እንደሆነ ዉሉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723/1/ ስር በተደነገገዉ መሰረት በሕግ ዉል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠዉ አካል ፊት ተደርጎ ያልተረጋገጠ ቢሆንም እንኳን ዉሉ ሕጋዊ ዉጤት እንደሚኖረዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 36887 እና በሌሎች መዛግብት ላይም አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

በተያዘው ጉዳይ  የአ.ብ.ክ.መ. ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ለመለወጥ ምክንያት ያደረገው  ተጠሪዎች የሽያጭ ውሉ ረቂቅ ነው በማለት ክደው የተከራከሩና በውል አዋዋይ ፊት ያልተደረገ በመሆኑ ህጋዊ ውል አለ የሚባልበት አግባብ የለም በማለት ነው፡፡ ሆኖም አመልካች ከተጠሪዎች ጋር የፈጸሙት የቤት ሽያጭ ውል መሰረት በማድረግ ያቀረቡት ክስ ላይ ተጠሪዎች የሰጡት መልስ በመካከላቸው የፀና ውል የሌለ መሆኑን ወይም በሕግ አግባብ አልተመዘገበም ከማለት ባለፈ በመካከላቸው ውል አለመኖሩን በመግለጽ በግልጽ ክደው ስለመከራከራቸው በስር ፍርድ ቤት አልተመለከተም፡፡ እንዲህ በሚሆን ጊዜ ደግሞ ዉሉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723/1 ስር በተደነገገዉ መሰረት በሕግ ዉል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠዉ አካል ፊት ተደርጎ ያልተረጋገጠ ቢሆንም እንኳን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 36887 በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ እንዳመላከተዉ በሰበር መ/ቁ/ 21448 ላይ በተሰጠዉ ትርጉም በመካከላቸው የቤት ሽያጭ ውል መኖሩን አምነው በውልና ማስረጃ አካል ባለመመዝገቡ ብቻ ውል የለም በሚል የሚቃወሙ ተከራካሪዎችን የሚያጠቃልል አይደለም፡፡ ምክንያቱም በፍ/ብ/ህግ ቁ 1723/1/ መሰረት የሚከናወነው የምዝገባ ዋና ዓላማ በተዋዋይ ወገኖች መካከል የቤት ሽያጭ ውል ለመኖሩ በማስረጃነት እንዲያገለግል በመሆኑ ነዉ፡፡ ስለሆነም ተጠሪዎች በመካከላቸው የቤት ሽያጭ ውል አለመሩን ክደው ባልተከራከሩበት ሥልጣን ባለው አካል አልተመዘገበም በሚል ውሉ ውጤት የለውም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ ስህተት ተፈጸመበት ሁኖ አግኝተነዋል፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪዎች ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት ሽያጭ ዉል የተደረገዉ የከተማ ቦታ የሊዝ መብት ማስተላለፍ የሚመለከት ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 18 እና 19 ስር እንደተደነገገዉ በሕጉ በተደነገገዉ አግባብ ሊራዘም የሚችል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በሊዝ የሚገኝ

የከተማ ቦታ የመጠቀም መብት ጸንቶ በሚቆይበት ዘመን በአዋጁ አንቀጽ 24/1 ስር በተደነገገዉ መሰረት ማንኛዉንም የሊዝ ባለይዞታ መብቱን ለማስተላለፍ ወይም በከፈለዉ የሊዝ ክፍያ መጠን በዋስትና ለማስያዝ ወይም በካፒታል አስተዋጽኦ ለመጠቀም እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ ሆኖም  እንዲሁም ማንኛዉም የሊዝ ባለይዞታ ከዉርስ በስተቀር ግንባታ ከመጀመሩ በፊት ወይም የግንባታዉን ግማሽ ከማጠናቀቁ በፊት የሊዝ መብቱን ማስተላለፍ የሚችለዉ አግባብ ባለዉ አካል ቁጥጥር ተደርጎበት ግልጽ የሸያጭ ሥርዓትን በመከተል እንደሆነ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 24/2 ስር የተደነገገዉ ሲሆን በሌላ አግባብ ስምምነት ካልተደረገ በስተቀር በመሬት የመጠቀም መብት…ሲተላለፍ በመሬቱ ላይ የተገነባዉ ሕንጻና ከሕንጻዉ ጋር የተያያዙ መገልገያዎች መብት አብሮ እንደሚተላለፍ… በአዋጁ አንቀጽ 24/6 ላይ ተመልክቷል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች ተጠሪዎች የሊዝ መብት ያገኙትን ቤትና ይዞታ በሽያጭ የማስተላለፍ ዉሉን እንዲፈጽሙ የቀረበ ስለሚሆን ተጠሪዎች አልተዋዋልንም በማለት በግልጽ ክደዉ ስለመከራከራቸው በስርፍርድ ቤቶች አለመረጋገጡን መሰረት በማድረግ በውሉ መሰረት እነዲፈጽሙ በስር ወረዳ እና ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ተወስኗል፡፡ ከላይ እንደተመለከተው የሊዝ መብት ማስተላለፍ ማለት መብቱ የተመሰረተበትን የከተማ ቦታና በእላዩ ላይ የሰፈረ ሕንጻ(ግንባታ) ጭምር የሚመለከት በመሆኑ የሊዝ መብት በሽያጭ ለማስተላለፍ የሚደረገዉ ዉል አግባብ ባለዉ አካል ቁጥጥር ተደርጎበት በጽሁፍ መሆንና በሕግ ዉል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠዉ አካል ፊት ተረጋግጦ የተመዘገበ መሆን የሚኖርበት ቢሆንም ተጠሪዎች በመካከላቸው የተፈጸመውን የሽያጭ ውል በግልጽ ክደው ያልተከራከሩ በመሆኑ በመካከላቸው የተፈጸመው ዉሉ ሕጋዊ ዉጤት የሚኖረው በመሆኑ ተጠሪዎች ይህንን መሰረት በማድረግ ያቀረቡትም መከራከሪያ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

በአጠቃላይ አመልካች ከተጠሪዎች ጋር ተዋዋልኩኝ ያሉትን ዉል ተጠሪዎች በግልጽ ክደዉ ያልተከራከሩ በመሆኑ የአ.ብ.ክ.መ. ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ለመለወጥ ምክንያት ያደረገው  ተጠሪዎች የሽያጭ ውሉ ረቂቅ ነው በማለት ክደው የተከራከሩና በውል አዋዋይ ፊት ያልተደረገ በመሆኑ ህጋዊ ውል አለ የሚባልበት አግባብ የለም በማለት የሰጠው ውሳኔ የፍ/ሕ/ቁ 1720፣1723 የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ 36887፣21448፣ 211204 እና ሌሎችም መዝገቦች ላይ የተሰጡትን ውሳኔዎች መሰረት ያላደረገ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሁኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚሁ መሰረት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ውሳኔ**

1. የአ.ብ.ክ.መ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 0339501 በቀን 21/03/2016 የላስታ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 0114953 ግንቦት 04 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠውንና የሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 40112 ሰኔ 14 ቀን 2015 ዓ.ም ያጸናውን ውሳኔ በመሻር የሰጠው

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ፍርድ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1//ሀ/መሰረት መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የላስታ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 0114953 ግንቦት 04 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠውንና የሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 40112 ሰኔ 14 ቀን 2015 ዓ.ም ያጸናውን ውሳኔ ጸንቷል፡፡
3. አመልካችና ተጠሪ በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

<u>**መዝገቡ ተዘግቷል**</u>፡፡

ፋ/ዘ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

የሰ.መ.ቁ. 256239

ህዳር 25 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

2. ቀነዓ ቂጣታ

3. ተሾመ ሽፈራዉ

4. ብርቅነሽ እሱባለዉ

5. ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች፡......መርከብ ሁለገብ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበር

ተጠሪ፡..........አቶ የሽዋስ ገደፍ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ይህ የዉዝፍ ደመወዝ ክፍያ ክርክር የተጀመረዉ በአማራ ክልል በባህር ዳር ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች የሥር ተከሳሽ፤ የአሁን ተጠሪ የሥር ከሳሽ ሆኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ አመልካች የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.03-122649 ህዳር 17 ቀን 2016 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ የአሁን ተጠሪ በሥር ወረዳ ፍ/ቤት ጽፈዉ ባቀረቡት የክስ አቤቱታ፡ ተጠሪ የአመልካች የዱቄት መኖ ማቀናባበሪያ ፋብሪካ ሥራ አስኪያጅ በመሆን በሥራ መሪነት ሳገለግል ቆይቼ ተጠሪ በሰጠዉ ጥቆማ በወንጀል ተጠርጥሬ ከአንድ ታስሬ ነጻ ተልቅቄ ወደ ሥራዬ የተመለስኩኝ ቢሆንም

ያለጥፋቴ የታሰርኩኝ በመሆኑ ያለተከፈለኝ ደመወዝ እና ደመወዝ ጭማሪ ከአመት እረፍት ጋር ታስቦ እንዲከለኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

የአሁን አመልካች በዚህ ላይ ባቀረበዉ መልስ አመልካች የቆሎ ግዥ እንደፈጸመ ተደርጎ በፎርጅት እትመት ሂሳብ ተሰርቶ 1.2 ሚሊዮን ብር በተጭበረበረ መንገድ መዘረፉን በኦዲተሮች በመረጋገጡ ለሚመለከተዉ አካል ጥቆማ መደረጉ ተገቢ ነዉ፤ አመልካች በዚህ መልክ ንብረቱ እንደተጭበረበረ ለፖሊስ ከማሳወቅ በቀር ተጠሪ አጭበርብሯል በማለት የሰጠዉ ጥቆማ የለም፤ ተጠሪ የሥራ መሪ በመሆናቸዉ አመልካች ወደ ሥራ ሊመልሳቸዉ ግዴታ ባይኖርበትም ወደ ሥራ መልሶታል፣ ተጠሪ ላልሰራዉ ሥራ የሚከለፈዉ ደመወዝ ሊኖር አይችልም፤ ተጠሪ ለታሰረዉ ጊዜ ደመወዝ እንዲከፈለዉ የሚደነግግ ሕግ የለም፣ ተጠሪ የሥራ መሪ በመሆኑ በፍትሕ ብሔር ሕጉም ሆነ በሥራ ዉሉ መሰረት ላልሰራዉ ሥራ ክፍያ የሚከፈልበት አግባብ የለም፤ የሰዉ ሃይል አደረጃጀት መመሪያ ቁጥር 54/2010 ይህን የሚፈቀድ አይደለም፣ በመሆኑም አመልካች በዚህ ጉዳይ የወንጀልም ሆነ የፍትሕ ብሔር ተጠያቂነት የለበትም ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ የወረዳዉ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመመርመር በሰጠዉ ዉሳኔ የአሁን ተጠሪ የሥራ መሪ በመሆኑ ጉዳዩ መታየት የለበት በፍትሕ ብሔር ሕጉ አግባብ በመሆኑ ከአንድ አመት በላይ ታስሮ ተጣርቶ በፍ/ቤት ነጻ ተብሎ ወደ ነበረበት ሥራዉ የተመለሰ ስለሆነ ያለአግባብ ታስሮ እያለ የተቋረጠበትን የአንድ አመት ደመወዙን በደመወዝ እስኬሉ መሰረት ተሰርቶ እንዲከፈለዉ በማለት ወስኗል፡፡ የባህር ዳርና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍ/ቤት የቀረበለትን ይግባኝ በትዕዛዝ ዉድቅ በማድረግ የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ደግሞ ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ የአሁን ተጠሪ ባልሰራዉ ወንጀል ተጠርጥሮ ታስሮ ከቆየ በኋላ በፍርድ ነጻ የተሰናበት በመሆኑ፣ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2540 እና በሕብረት ሥራ ማህበራት የሰዉ ሃይል አደረጃጀትና አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 54/2010 አንቀጽ 6 (6) መሰረት ተጠሪ ሥራዉን ያልሰራዉ በበቂና አሳማኝ ምክንያት በመሆኑ የአንድ አመት ደመወዝ እንዲከፈለዉ መወሰኑ ተገቢ ነዉ በማለት የሥር ፍ/ቤቶችን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች በ10/04/2016 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ የአሁን ተጠሪ የተቀጠረዉ በአሰሪዉና በሥራ መሪዉ መካከል በተደረገዉ የሥራ ዉልና የፍትሕ ብሔር ሕግ ቁጥር 2512 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች እንጂ የሰዉ ሃይል መመሪያ ቁጥር 54/2010 አንቀጽ 6 (6) ድንጋጌ በዚህ ጉዳይ ላይ ተፈጻሚነት የለዉም፡፡ አመልካች ተጠሪዉ የገንዘብ ማጭበርበር ወንጀል ፈጽሟል በሚል ለፖሊስ ጠቁሞ ያስያዘዉ ነገር የለም፤ በዚህ ረገድ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ነገር የለም፡፡ የክልሉ ሰበር ችሎት ተጠሪ ወንጀል ፈጽሟል በሚል ጠቁማችሁ ስላስያዛችሁ በመመሪያ ቁጥር 54/2010 አንቀጽ 6 (6) መሰረት ተጠሪ ከሥራ የቀረዉ አሳማኝ በሆነ ምክንያት ነዉ በሚል የሰጠዉ ዉሳኔ ከተሰጠዉ ስልጣን ዉጭ የተወሰነ ጉዳይ

ነዉ፡፡ ተጠሪ የሥራ መሪ በመሆኑ፣ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በሚደረጉት ግንኙነቶች የሰዉ ሃይል መመሪያ ቁጥር 54/2010 ዓ.ም ተፈጻሚነት የለዉም፡፡ መመሪያዉ ተፈጻሚነት አለዉ ቢባል እንኳን በወንጀል ተጠርጥሮ መታሰር እንደአሳማኝ ምክንያት የሚወሰድ አይደለም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልን በማለት አመልክቷል፡፡

ይህ ሰበር ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣አመልካች ላልተሰራ ሥራ ደመወዝ እንዲከፈል መወሰኑ ሕጉን መሰረት ያደረገ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ሲባል የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ባዘዘዉ መሰረት በ26/07/2016 ዓ.ም በተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት ባጭሩ፡ የአማራ ክልል የሕብረት ሥራ ማህበራት የሰዉ ሃይል አደረጃጀትና አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 54/2010 በሰራተኞች፣ በሥራ መሪዎች እና በኃላፊዎች ላይ ተፈጻሚነት ያለዉ መሆኑን ከመመሪያ መረዳት የሚቻል በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበዉ መከራከሪያ ዉድቅ እንዲደረግልኝ፤ አመልካች ዩኒዬን ተጠርጣሪ ሊሆን የሚገባዉን አካል በአግባቡ ላይቶ መረጃና ጥቆማ ባለመስጠቱ ምክንያት ያለጥፋቴ የታሰርኩኝ በመሆኑ በመመሪያዉ አንቀጽ 6 (6) መሰረት በሥራ ቦታ ያልተገኘሁት በአሳማኝና በበቂ ምክንያት መሆኑን ተወስዶ ያልተከፈለኝ ደመወዝ እንዲከፈለኝ መወሰኑ ተገቢ ነዉ፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ ተገቢ ስለሆነ እንዲጸናልኝ በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካች በ10/8/2016 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክርና ለሰበር ቅሬታዉ መነሻ የሆኑትን የሥር ፍ/ቤቶችን ዉሳኔዎች አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ የአሁን ተጠሪ በአመልካች ዩኒዬን የዱቄት መኖ ማቀናባበሪያ ፋብሪካ ሥራ አስኪያጅ በመሆን በሥራ መሪነት ማህበሩን ሲያገለግል መቆየቱ ግራ ቀኙን የላከራከረና በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ነዉ፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ አመልካቾ በዩኒዬኑ ገንዘብ ላይ የማጭበርበር የወንጀል ድርጊት ተፈጽሟል በሚል ለሚመለከተዉ የፖሊስ አካል ጥቆማ በመስጠቱ፣ የፖሊስ አካል ደግሞ በሕግ በተሰጠዉ ስልጣን እና የወንጀለኛ መቅጫ ስነስርዓት ሕጉ በሚፈቅደዉ አግባብ ተጠሪን በወንጀል ድርጊቱ ጠርጥሮዉ በቁጥጥር ስር በማዋል፣ ተጠሪ የታሰረ ሲሆን፣ የሚመለከተዉ ዐቃቤ ሕግ ደግሞ በተጠሪ ላይ ክስ አቅርቦ ሲከራከሩ ከቆዩ በኂላ ተጠሪ ይህን የወንጀል ድርጊት ለመፈጸሙ በፍርድ ቤት በተሰጠዉ ፍርድ በመረጋገጡ ከማረሚያ መለቀቁን መዝገቡ ያሳያል፡፡ ይህን ተከትሎ አመልካች የአሁን ተጠሪን ወደ መደበኛ ሥራዉ በመመለስ ተጠሪ ሥራዉን እየሰራ እንደሚገኝ የሥር ፍ/ቤት የዉሳኔ ግልባጭ ያመለክል፡፡

ነገር ግን ግራ ቀኛቸዉን ያከራከረዉ ተጠሪ በህግ ቁጥጥር ስር ዉሎ ታስሮ ለቆየበት ጊዜ ዉዝፍ ደመወዝ ሊከፈለዉ ይገባል ወይስ ይገባዉም የሚለዉ ነጥብ ነዉ፡፡ በዚህ ረገድ ተጠሪ ባቀረበዉ ክርክር ያለጥፋቴ የታሰርኩት አመልካች ተጠርጣሪዉን በሚገባ ላይቶ ጥቆማ በማድረጉ ያለአግባብ ለአንድ አመት የታሰርኩኝ

ስለሆነ ዉዝፍ ደመወዝ ሊከፈለኝ ይገባል በሚል ጠየቀ ሲሆን፤ የአሁን አመልካች በበኩሉ ባቀረበዉ ክርክር በዩኒዬኑ ገንዘብ ላይ የማጭበርበር ወንጀል በመፈጸሙ በሕግ አግባብ ለሚመለከተዉ ፖሊስ ሪፖርት ማድረግ የሕግ ግዴታ በመሆኑ፣ አመልካች ኃላፊነት የለበትም፤ ተጠሪ ላልሰራዉ ሥራ ደመወዝ የሚከፈልበት አግባብ የለም በማለት ተከራክሯል፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ ባቀረበዉ ክርክር ደመወዝ ሊከፈለኝ ይገባል በማለት የሚከራከረዉ የአማራ ክልል የሕብረት ሥራ ማህበራት የሰዉ ሃይል አደረጃጀትና አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 54/2010 አንቀጽ 6 (6) መሰረት ያለጥፋቴ የታሰርኩኝ በመሆኑ አሳማኝና በቂ ምክንያት በመሆኑ ለታሰርኩበት ጊዜ ዉዝፍ ደመወዝ ሊከፈለኝ ይገባል የሚል ሲሆን፤ አመልካች በበኩሉ ተጠሪ የሥራ መሪ በመሆኑ ተፈጻሚነት ያለዉ የሥራ ዉል እና የፍትሐ ብሔር ሕጉ ድንጋጌዎች እንጂ የመመሪያ ቁጥር 54/2010 አንቀጽ 6 (6) ድንጋጌ አይደለም፤ ተጠሪ ላልሰራዉ ሥራ ዉዝፍ ደመወዝ ሊከፈለዉ አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ አንጻር ምላሽ ማግኘት ያለበት በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ባለዉ ክርክር ተፈጻሚነት ያለዉ የፍትሐ ብሔር ሕጉ ድንጋጌዎች እና የሥራ ዉል ነዉ ወይስ የሰዉ ሃይል መመሪያ ቁጥር 54/2010 አንቀጽ 6 (6) ድንጋጌ ነዉ? ተጠሪ ታስሮ ለነበረዉና ስራ ላልሰራ ጊዜ ያልተከፈለዉ ዉዝፍ ደመወዝ ሊከፈለዉ ይገባል ወይስ አይገባም የሚለዉ ነጥብ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

**የመጀመሪያዉ ነጥብ በተመለከተ፡**

ከፍ ሲል እንደተጠቀሰዉ ተጠሪ በአመልካች ማህበር የዱቄት መኖ ማቀናባበሪያ ፋብሪካ ሥራ አስኪያጅ በመሆን በሥራ መሪነት ሲሰራ ነበር፡፡ እንደሚታወቀዉ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 3 (2) (ሐ) መሰረት አዋጁ ሰራተኛዉ የሥራ መሪ እንደሆነ ተፈጻሚነት እንደሌለዉ ያመለክታል፡፡ በአሠሪ እና በሥራ መሪ መካከል ባለዉ የሥራ ግንኙነቶች ላይ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ተፈጻሚነት እንደማይኖረዉ ነዉ፡፡ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ያለዉ ግንኙነት የሚገዛዉ በግራ ቀኙ መካከል በተደረገዉ የሥራ ዉል እና የፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ 2512 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሆኑን ግልጽ ነዉ፡፡ ስለሆነም ተጠሪ በሥራ ዉሉ ላይ የተመለከተዉን ግዴታዉን የመወጣት ኃላፊነት እና በዉሉ የተጠቀሰዉን ደመወዝ የማግኘት መብት ያለዉ ሲሆን፣ አመልካች ደግሞ በዉሉ መሰረት ሥራዉ እንዲሰራ የመጠየቅ መብት እና በዉሉ ላይ የተመለከተዉን ደመወዝ ለተጠሪ ለመክፈል ግዴታ ይኖርበታል ማለት ነዉ፡፡ ተጠሪ ለሰራዉ ሥራ ደመወዝ የማግኘት መብት ያለዉ ሲሆን፣ አመልካች ደግሞ በተጠሪ ለተሰራለት ሥራ ለተጠሪ ደመወዝ የመክፈል ግዴታ ይኖርበታል፡፡ ተጠሪ ላልሰራዉ ሥራ ደመወዝ መጠየቅ አይችልም፤ አመልካች ደግሞ ላልተሰራ ስራ ደመወዝ ለመክፈል አይገደድም፡፡ ይህም ደግሞ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ.2512፣ 2523፣ 2534 እና 2540 ድንጋጌዎችን ይዘትና ዓላማ ማየት ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል የአማራ ክልል የህብረት ሥራ ማህበራት የሰዉ ኃይል አደረጃጀትና አስተዳደር መመሪያ 54/2010 አንቀጽ 6 (6) ድንጋጌ በአመልካች እና የሥራ መሪ በሆነዉ በአሁን ተጠሪ መካከል ያለዉ ዉዝፍ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

ደመወዝ እንዲከፈለኝ የሚለዉ ጥያቄ ላይ ተፈጻሚነት አለዉ ወይስ የለዉም? የሚለዉ ነጥብ መታየት ያለበት ጉዳይ ነዉ፡፡ የመመሪያ የትርጉም ክፍል ለሰራተኛ ትርጉም በመስጠት የሥራ መሪን የሚያካተት መሆኑን የሚያመለክት አይደለም፡፡ በዚህ መመሪያ ትርጉም ክፍል ‹‹የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ›› ትርጉም መስጠቱ ሲታይ መመሪያዉ ያልሸፈናቸዉን ጉዳዮች አዋጁ ተፈጻሚነት እንደሚኖረዉ ያስገነዝባል፡፡ የመመሪያ አጠቃላይ በሰራተኛ ቅጥር፣ እድገት፣ ዝዉዉር፣ ስንብት፣ የዲሲፕሊን እርምጃዎችን የሚመለከቱ ጉዳዮች የያዘ ነዉ፡፡ የመመሪያ አንቀጽ 2.2.1 ድንጋጌ ስለ ሥራ አስኪያጅ ቅጥር የሚመለከት መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡ እንዲሁም የመመሪያዉ አንቀጽ 4.21 (ሀ) የሥራ አስኪያጅን ተግባርና ኃላፊነትን የሚዘረዝር ሲሆን የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (ለ) ደግሞ የምክትል ሥራ አስኪያጅ ተግባርና ኃላፊነትን ይዘረዝራል፡፡ የመመሪያ አንቀጽ 5.1 በዩኒዬን ደረጃ ያሉትን የሥራ መደቦችን የሚዘረዝር ሆኖ ከዚህ ዉስጥ የሥራ አስኪያጅ እና የምክትል ሥራ አስኪያጅ የሥራ መደቦች ተመልክቶ እናገኛለን፡፡ ይሁን እንጂ በመመሪያዉ አንቀጽ 11.2 መሰረት የሥራ መሪ ባህሪ ያላቸዉ የህብረት ሥራ ማህበራት ሰራተኞች በፍትሐ ብሔር ሕግ መሰረት ከሕብረት ሥራ ማህበሩ ጋር በሚያዙት የሥራ ዉል መሰረት የሚፈጸም መሆኑን ይደነግጋል፡፡

በዚህ መሰረት አሁን ግራ ቀኙን ያከራከረዉ የመመሪያዉ ድንጋጌ አንቀጽ 6 (6) በዚህ ጉዳይ ላይ ተፈጻሚነት አለዉ ወይስ የለዉም? የሚለዉ ነጥብ መታየት ያለበት ጉዳይ ነዉ፡፡ ተጠሪ ባቀረበዉ ክርክር ያለአግባብ የታሰርኩኝ ስለሆነ በዚህ ደንጋጌ መሰረት ከሥራ የቀረሁበት ምክንያት አሳማኝና በቂ ምክንያት በመሆኑ ዉዝፍ ደመወዝ ሊከፈለኝ ይገባል የሚል ሲሆን፤ አመልካች ደግሞ ይህ ድንጋጌ በግራ ቀኙ ግንኙነት ተፈጻሚነት የለዉም፣ ተፈጻሚነት አለዉ ቢባል እንኳን ተጠሪ መታሰሩ ላልሰራዉ ሥራ ደመወዝ እንዲከፈለዉ አሳማኝና በቂ ምክንያት ነዉ ሊባል አይችል በማለት ተከራክሯል፡፡ የዚህ ደንጋጌ ርዕስ እና ይዘት ሲታይ ስለሰራተኛ ደመወዝና ጥቅማ ጥቅሞችን የሚመለከተወ ነዉ እንጂ ስለሥራ አስኪያጅ የሚመለከት አይደለም፡፡ በዚህ ድንጋጌ ሥር ለሰራተኛዉ ደመወዝ የሚከፈለዉ በመመሪያዉ መሰረት መሆን አለበት፣ ደመወዝም መከፈል ያለበት ለተሰራዉ ሥራ ብቻ መሆን እንደለበት፣ የሰራተኛዉ ደመወዝ በመመሪያዉ መሰረት ጸድቅ ተፈጻሚ የሚሆነዉ የሥራ አመራር ኮሚቴ/ቦርድ ሊቀመንበር ወይስ ሥራ አስኪያጅ በተሰጠዉ ዉክልና መሰረት እንደሆነ ይደነግጋል፡፡ በመመሪያዉ አንቀጽ 6 (6) ደንጋጌ መሰረት ‹‹ማንኛዉም ሠራተኛ አሳማኝ ባልሆነ ምክንያትና በቂ ባልሆነ ማስረጃ ከሥራ ለቀረበት ጊዜ ደመወዝ እንደማይከፈለዉ›› ይደነግጋል፡፡ ነገር ግን ይህ ድንጋጌ በሰራተኛ ላይ እንጂ በሥራ መሪ ላይ ባለመሆኑ፣ አሰመልካች የአሁን ተጠሪ ያለአግባብ በታሰረ ጊዜ ላልሰራዉ ሥራ ዉዝፍ ደመወዝ ለተጠሪ መክፈል አለበት ወይስ የለበትም፣ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ምክንያቱን መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ይህን ድንጋጌ መሰረት በማድረግ ተጠሪ ያለአግባብ ለታሰረበት ጊዜ እንደአሳማኝና በቂ ምክንያት ተወስዶ አመልካች ዉዝፍ ደመወዝ ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል የማለት ያሳለፈዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ተቀባይነት የለዉም ብለናል፡፡

**ሁለተኛ ነጥብ በተመለከተ፡**

የአሁን ተጠሪ በወንጀል ተጠርጥረዉ በቁጥጥር ስር ዉሎ ታስሮ ለቆየዉ ጊዜ አመልካች ዉዝፍ ደመወዝ ሊከፍለዉ ይገባል ወይስ አይገባዉም የሚለዉ ነጥብ መታየት ያለበት ነዉ፡፡ በዚህ መሰረት አመልካች በማህበሩ ላይ የገንዘብ ማጭበርበር ወንጀል መፈጸሙን የኦዲት ሪፖርት በማመልከት ይህን ጉዳይ ለሚመለከተዉ የፖሊስ አካል ጥቆማ ማድረጉን ተከትሎ ፖሊስ ተጠሪን በቁጥጥር ስር በማዋል ምርመራ በማድረግ፣ የክልሉ ዐቃቤ ሕግ ደግሞ የሙስና ወንጀል ክስ በተጠሪ ላይ በማቅረቡ ተጠሪ ለአንድ አመት መታሰሩን የሥር ፍ/ቤት የዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ ይሁን እንጂ ፍ/ቤት በሰጠዉ ፍርድ ተጠሪ የወንጀል ኃላፊነት የለበት በመሆኑ ተረጋግጦ በነጻ ከማረሚያ መለቀቁን መዝገቡ ያሳያል፡፡ አመልካች በማህበሩ ገንዘብ ላይ የማጭበርበር ወንጀል ተፈጽሟል የሚል ከሆነ ለፖሊስ ጥቆማ መስጠት የሚከለክለዉ የህግ የለም፡፡ በዚህ አግባብ ጥቆማ የደረሰዉ ፖሊስ በሕግ በተሰጠዉ ስልጣንና በወንጀለኛ መቅጫ ስነስርዓት ሕግ መሰረት ተገቢን የወንጀል ምርመራ በማድረግ ተጨባጭ ማስረጃ ያገኘ እንደሆነ፣ ተጠሪ ቁጥጥር ስር በማዋል እና የምርመራ መዝገቡን ለዐቃቤ ሕግ በማስተላለፍ ዐቃቤ ሕግ ደግሞ ክስ ለማቅረብ በቂና አሳማኝ ማስረጃ መኖሩን ያረጋገጠ እንደሆነ በተጠሪ ላይ ክስ ለማቅረብ ስልጣን ይኖረዋል፡፡ እንግዲህ አመልካች በዚህ አግባብ የወንጀል ድርጊት ለሚመለከተዉ አካል ጥቆማ ከሰጠ በኋላ ጉዳዩን የሚመሩት በሕግ ስልጣን የተሰጣቸዉ የፍትሕ አካላት ማለትም ፖሊስ፣ ዐቃቤ ሕግ እና ፍ/ቤት እንጂ አመልካች በዚህ ጉዳይ ላይ ቁጥጥር ይኖረዋል ተብሎ አይገመትም፡፡ እነዚህ የፍትሕ አካላት በሕግ በተሰጠዉ ስልጣን መሰረት ጉዳዩን አጣርተዉ የተፋጠነ ፍትሕ የመስጠት ኃላፊነት አለባቸዉ፡፡ የፍትሕ አስተዳደር ሥርዓቱ ባስከተለዉ መጓተት ምክንያት የተጠሪ መብት የተጎዳ ቢሆንም አመልካች ይህን ኃላፊነት የሚሸከምበት አግባብ የለም፡፡ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰዉ አመልካች ለተጠሪ ደመወዝ ለመክፈል የሚገደደዉ ለተሰራ ሲሆን፣ ተጠሪም ለሰራዉ ስራ ደመወዝ የማግኘት መብት አለዉ፡፡ አመልካች ላልተሰራ ሥራ ለተጠሪ ደመወዝ የመክፈል ኃላፊነት የለበትም፡፡ በዚህ ረገድ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተደረገዉን የሥራ ዉል እና የፍ/ብ/ሕ/ቁ.2512፣ 2523፣ 2534 እና 2540 ድንጋጌዎችን ይዘትና ዓላማ ማየት ይቻላል፡፡ተጠሪ በሥራ ቦታ ተገኝቶ ሥራዉን ለመስራት ዝግጁ ሆኖ እያለ በራሱ ጉድለት ባልሆነ ምክንያት ስራ መስራት ያልቻለ እንደሆነ አመልካች ለተጠሪ ደመወዝ የማይከፍልበት የህግ አግባብ አይኖርም፡፡ አሁን በተያዘዉ ጉዳይ ተጠሪ በሥራ ቦታ ተገኝቶ ለሥራ ዝግጁ ባልሆነበት በወንጀል ተጠርጥሮ ታስሮ ለነበረ ጊዜ አመልካች ላልተሰራ ሥራ ለተጠሪ ደመወዝ የሚከፍለበት የህግ አግባብ የለም፡፡

ስለሆነም የሥር የወረዳዉ እና የከፍተኛ ፍ/ቤቶች ተጠሪ ያለአግባብ የታሰረ በመሆኑ የአንድ አመት ዉዝፍ ደመወዝ እንዲከፈለዉ በማለት ያሳለፉት ዉሳኔ የህግ መሰረት የለዉም፡፡ እንዲሁም የክልሉ ሰበር ችሎት አመልካች ያለአግባብ ተጠሪ ላይ የወንጀል ጥቆማ በማድረጉ ተጠሪ ያለጥፋቱ ለአንድ አመት የታሰረ በመሆኑ በሰዉ ሃይል መመሪያ ቁጥር 54/2010 አንቀጽ 6 (6) መሰረት ተጠሪ ከሥራ የቀረዉ አሳማኝና

በቂ ምክንያት እንደሆነ ስለሚቆጠር አመልካች ለተጠሪ ዉዝፍ ደመወዝ እንዲከፍለዉ በማለት የወሰነዉ ተቀባይነት የለዉም፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች ተጠሪ ለሥራ ዝግጁ ሆኖ በሥራዉ ቦታ ባልተገኘበት በወንጀል ጉዳይ ታስሮ በቆየበት ሁኔታ በሥራ ቦታ ተገኝቶ የሰራዉ ስራ በሌለበት አመልካች ለተጠሪ ዉዝፍ ደመወዝ እንዲከፍለዉ መወሰናቸዉ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1. የባህር ዳር ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ.82890 በ3/6/2015 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የባህር ዳርና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.03-35516 በ29/6/2015 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.03-122649 ህዳር 17 ቀን 2016 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች የአሁን ተጠሪ በእስር ለቆየበት ጊዜ ዉዝፍ ደመወዝ ለመክፈል አይገደድም ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኛቸዉ የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ የራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

- ይህ ሰበር ችሎት በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ የአፈጻጸም የእግድ ትዕዛዝ በዚህ ዉሳኔ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
- የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ፋ/ዘ**

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

የሰ.መ.ቁ.257068

ህዳር 26 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች፡……1. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

2. ቀነዓ ቂጣታ

3. ተሾመ ሽፈራዉ

4. ብርቅነሽ እሱባለዉ

5. ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች፡ ……..ወ/ሮ ቃልኪዳን አስቻለዉ ጸጋሁን - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡……………ክሮስ ካንትሪ ትሬዲንግድ ኃ/የተ/የግ/ማህበር - የቀረበ የለም

ይህ መዝገብ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ይህ የሥራ ስንብት ክርክር የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች የሥር ከሳሽ፣ የአሁን ተጠሪ የሥር ተከሳሽ ሆኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.307021 በ05/02/2016 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ የአሁን አመልካች በሥር ፍ/ቤት ጽፈዉ ባቀረቡት የክስ አቤቱታ፡ አመልካች በተጠሪ ድርጅት በቴክኒካል ማናጀርነት የሥራ መደብ ተቀጥሬ እየሰራሁኝ እኔ ከመቀጠሬ በፊት የተገዙና ባለማካርኩት መድሃኒቶች ሽያጭ ኪሳራ ደርሷል በሚል ህዳር 16 ቀን 2015 ዓ.ም በጻፈ ማስጠንቀቂያ ከአንድ ወር በኋላ የሥራ ዉሌ እንደሚቋረጥ አሳዉቆኝ የሥራ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

ዉሉን ያቋረጠ በመሆኑ፣ ስንብቱ ሕገወጥ ነዉ እንዲባልልኝ፣ የተለያዩ ክፍያዎችን እንዲከፍለኝ እንዲወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

የአሁን ተጠሪ በዚህ ክስ ላይ ባቀረበዉ መልስ አመልካች የተቀጠሩት የኢትዮጵያ ምግብና መድሀኒት ባለስልጣን በሰጣቸዉ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ መሰረት ያደረገ በመሆኑ እሳቸዉ ያስገዙትም ሆነ ተገዝቶ የተረከቡትን መድሐኒት ጊዜዉ ሳያልፍበት እንዲሸጥ ተቀጥረዉ እያሉ ይህን ሳያደርጉ መድሐኒት ጊዜዉ ያለፈበት በመሆኑ ከጥቅም ዉጭ ስለሆነ ብር አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሰማንያ አራት ሺህ  በተጠሪ ላይ ኪሳራ የደረሰዉ በአመልካች ጥፋት በመሆኑ፣ አመልካችን በማሳመን ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸዉ ያሰናበትናቸዉ በመሆኑ ስንብቱ ሕጋዊ ነዉ፣ የተጠየቀዉ ክፍያ ተቀባይነት የለዉም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኂላ የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካችን የምስክርነት ቃል እና የተጠሪዎችን ምስክሮች በመስማት ማስረጃን በመመርመር በሰጠዉ ዉሳኔ ተጠሪ የኢትዮጵያ ምግብና መድሀኒት ባለስልጣን በድረ-ገጽ የገለጸዉን የሥራ መዘርዝር እንጂ ለአመልካች የሥራ መዘርዝር የሰጠዉ ነገር የለም፣ አመልካች ያለባቸዉን ኃላፊነት በግልጽ ያላስረዳና ለአመልካችም ኃላፊነታቸዉን ያሳወቀዉ ነገር ባለመኖሩ አመልካች ጊዜ ላለፈባቸዉ መድሐኖቶች ኃላፊነት የለባቸዉም፤ ስለዚህ ስንብቱ ሕገወጥ ነዉ፤ ተጠሪ ለአመልካች የተለያዩ ክፍያዎችን እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን ተጠሪ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ አመልካች በራሷ በሰጣችዉ የምስክርነት ቃል የተገዙ  መድሃኖቶች ማረጋገጥ፣ መድሃኒቶች ሲሸጡ ትክክለኛ መጠን መዉጣቱን ማረጋገጥ፣ የመድሃኒቶች ማከማቻ ቦታቸዉን ማረጋገጥ፣ የመድሃኒቶች ሎጅስቲክን ማረጋገገጥና የጥቅም ጊዜያቸዉ ያለፈባቸዉን መድሃኒቶች የማሳወቅ ግዴታ ያለባት መሆኑን ማሳወቋን ያስረዳች ሲሆን፣ የተጠሪ ምስክሮች ደግሞ የአመልካችን የሥራ መዘርዝር የሚሰጣት የሙያ ፈቃዷን የሰጣት የኢትዮጵያ ምግብና መድሃኒት ቁጥጥር ባለስልጣን መሆኑን በዚህ መሰረት የመድሃኒቶችን ሁኔታ የመቆጣጠሪና የመሸጥ እንዲሁም የጥቅም ጊዜያቸዉ ያለፈባቸዉን መድሃኒቶች ቀድሞ ሪፖርት የማድረግ ግዴታ ያለባቸዉ መሆኑን ያስረዱ በመሆኑ፣ አመልካች በዚህ መሰረት ግዴታቸዉን ያልተወጡ በመሆናቸዉ ተጠሪ በዚህ ምክንያት አመልካችን ከሥራ ያሰናበታቸዉ በመሆኑ ስንብቱ ሕጋዊ ነዉ፤ አመልካች ያልተጠቀሙበት የእረፍት ክፍያ በስተቀር ሌሎች ክፍያዎች ሊከፈላት

አይገባም በማለት የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች ታህሳስ 26 ቀን 2016 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ ተጠሪ አመልካችን ከሥራ ያሰናበታት ኃላፊነቷን በአግባቡ አልተወጣችም የሚል በመሆኑ ይህ ደግሞ የአቅም ጉዳይ ስለሆነ በአመልካች የሥራ መዘርዝር አግባብ የተደረገ የሥራ ምዘና በሌለበት የሥር ፍ/ቤት የሥራ ዉሉን ያቋረጠዉ በአግባቡ ነዉ በማለት ያሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፤ በተጠሪ ላይ የደረሰዉ ጉዳት በማስረጃ አልተረጋገጠም፤ ስለሆነም የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲሻርልኝ በማለት በዝርዝር አመልክቷል፡፡

ይህ ሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ባዘዘዉ መሰረት በ14/10/2016 ዓ.ም በተጻፈ መልስ፡ የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት በዚህ ጉዳይ የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት በመሆኑ እንዲጸናልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ አመልካች ሐምሌ 10 ቀን 2016 ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር እና ለሰበር አቤቱታዉ መነሻ የሆነዉ የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ በዚህ ጉዳይ ምላሽ ማግኘት ያለበት ጉዳይ ፣የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ የአመልካችን የሥራ ዉል በማቋረጥ ከሥራ ያሰናበታት በሕጋዊ መንገድ ስለሆነ ስንብቱ ሕጋዊ ነዉ በሚል ያሳለፈዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በዚህ መሰረት አመልካች በተጠሪ ድርጅት የተቀጠሩት ከኢትዮጵያ ምግብና መድሃኒት ቁጥጥር ባለስልጣን በተሰጣቸዉ የሙያ ፈቃድ መሰረት በማድረግ ሲሆን አመልካችም ሆነ የተጠሪ ምስክሮች በሰጡት የምስክርነት ቃል አመልካች የመድሃኒቶችን ሁኔታ የመቆጣጠሪና የመሸጥ እንዲሁም መድሃኒቶች የመጠቀሚያ ጊዜያቸዉ ሳያልፍ ለተጠሪ ቀድሞ ሪፖርት የማድረግ ግዴታ እንዳለባቸዉ የተረጋገጠ ጉዳይ ነዉ፡፡ በዚህ ምክንያት መድሃኒቶቹ የመጠቀሚያ ጊዜያቸዉ በማለፉ በተጠሪ ላይ የገንዘብ ኪሳራ ጉዳት የደረሰ መሆኑን በኦዲት ሪፖርት የተረጋገጠ መሆኑን የተጠሪ ምስክሮች ማስረዳታቸዉን ከሥር ፍ/ቤት የዉሳኔ ግልባጭ ማየት ይቻላል፡፡ አመልካች በበኩላቸዉ አግባብነት ያለዉን ማስረጃ በማቅረብ ይህን የተጠሪን ማስረጃ ያስተባበሉበት ሁኔታ መኖሩን መዝገቡ አያሳይም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ተጠሪ

የአመልካችን የሥራ ዉል በማቋረጥ ከሥራ ያሰናበታቸዉ በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 27 (1) (ሸ) መሰረት በመሆኑ፣ ስንብቱ ሕጋዊ ነዉ ከሚባል በስተቀር ስንብቱ ሕገወጥ ነዉ የሚባልበት የሕግ አግባብ የለም በማለት የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ የሚነቀፍበት የህግ ምክንያት የለም ብለናል። ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ. 64988፣ 104294 እና በሌሎች መዛግብት ላይ የሰጠዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ዉሳኔዎች አንጻር ሲታይ የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት መሆኑን ያስገነዝባል።

ስለሆነም በዚህ ጉዳይ የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል በተያዘዉ ጭብጥ ላይ የተጠቀሰዉ የአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 27 (1) (ሠ) ለዚህ ጉዳይ አግባብነት የሌለዉ በመሆኑ ተቀባይነት የለዉም ብለናል። እንዲሁም አመልካች ከዚህ አንጻር ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ከፍ ሲል በተጠቀሰዉ ምክንያት ተቀባይነት የለዉም ብለናል።

ሲጠቃለል የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ የአመልካችን የሥራ ዉል በማቋረጥ ከሥራ ያሰናበታት በሕጋዊ መንገድ ነዉ፤ ስንብቱ ሕጋዊ ነዉ በማለት የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በመሻር ያሳለፈዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል።

**<u>ዉሳኔ</u>**

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.307021 በ05/02/2016 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9 (1) መሰረት ጸንቷል።
2. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ።
3. ግራ ቀኛቸዉ የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

**<u>ማስታወሻ፡</u>** - ይህ የሰበር ችሎት ዉሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

የሰበር መ/ቁ 257342

ህዳር 24 ቀን 2017 ዓ/ም

ዳኞች - ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርቅነሽ እሱባለዉ

አመልካች ፡- ዊነርስ ቻፕል ኢንተርናሽናል አልቀረቡም

ተጠሪዎች ፡- 1. አቶ አለማየሁ ወዳጅ መንግስቱ

2. አቶ ፀጋዩ ማሞ ገ/ፃዲቅ

3. አቶ ፍቅሩ ተስፋ በቃና

ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ የስራ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረዉ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪዎች በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው ተጠሪዎች ባቀረቡት ክስ ከአመልካቸ ጋር የነበራቸዉ የስራ ግንኙነት የተቋረጠ በመሆኑ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸዉ የጠየቁ ሲሆን አመልካች በቀረበዉ ክስ ላይ መልስ እንዲያቀርብ ትዕዛዝ ተልኮ ነገር ግን ተጠሪዎች አመልካች መጥሪያ ለመቀበል ፍቃደኛ አለመሆኑን በቃለ መኃላ አረጋግጠዉ በመቅረባቸዉ ፍርድ ቤቱ የአመልካች በፁሁፍ መልስ የማቅረብ መብቱን አልፎ ክስ ለመስማት በተቀጠረበት ቀንም አመልካች ባለመቅረቡ ጉዳዩን አመልካች በሌለበት አከራክሮ ውሳኔ

ሰጥቷል፡፡ በሰጠው ውሳኔ የስራ ውሉ የተቋረጠው በተጠሪዎች በራሳቸው ፈቃድ መሆኑን፤ እንዲሁም ክፍያን አስመልክቶ የሁለት አመት የትርፍ ሰዓት ክፍያን ጨምሮ የተለያዩ ክፍያዎች ለተጠሪዎች እንዲከፈል ወስኗል፡፡

ከዚህ በኃላ አመልካች በሌለሁበት የተሰጠ ዉሳኔ ይነሳልኝ በማለት አመልክቶ ፍርድ ቤቱ የአመልካች አቤቱታ ላይ ግራቀኝን ካከራከር እና ማስረጃ ከሰማ በኃላ አመልካች የፍርድ ቤቱን መጥርያ ደርሶት እያለ መቅረብ ሲገባዉ ለ3 ግዜ መጥሪያ አንቀበልም ለቅርንጫፍ ቢሮ አቅርቡ እያለ መመለሱ በማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች መከሰሱን አዉቆ መልስ ለመስጠት ያልፈለገ እንደሆነ የሚያስቆጥር በመሆኑና ተጠሪዎች መጥርያ አላደረሱም የሚባልበት ሁኔታ ባለመኖሩ የአመልካች አቤቱታ ተቀባይነት የለውም በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ዉሳኔና ብይን ቅር ተሰኝቶ ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱ የቀረበዉን ይግባኝ አቤቱታ መርምሮ በፍ/በ/ስ/ስ/ህ/ቁ 337 መሰረት ይግባኙን ሰርዟል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው፡፡ አመልካች ጥር 02 ቀን 2016 ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የአመልካች ምክትል አስተዳዳሪ መጥሪያው ደርሷቸው ወደአየር ጤና ሂዱና ስጡ ማለታቸውን የስር ፍ/ቤቶች አረጋግጠው ነገር ግን ይህ መጥሪያው በአግባቡ ደርሶታል አየር ጤና ሄዳችሁ ስጡ ማለቱ አልቀበልም ከማለት ጋር እኩል ውጤት አለው በማለት መወሰኑ በህገመንግስቱ የተረጋገጠልኝን የመሰማት መብት ያላረጋገጠ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡ የስር ፍ/ቤቶች መጥሪያውን ለሚመለከተው ሄዳችሁ ስጡ ባለው ምክትል አስተዳዳሪ ምክንያትና ሃሰተኛውን የተጠሪዎች ቃለመሃላ መሰረት አድርገው የአመልካችን መብት ማለፋቸው የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታም ይገባል፣

የስር ፍርድ ቤት ያሳለፈው ብይን ላይ ያቀረብነዉ አቤቱታ ዉድቅ ነው የሚባልበት የህግ ምክንያት የለም እንጂ ብይኑ የህግ ስህተት አልተፈፀመበትም የሚባል ቢሆን እንኳን የስር ፍ/ቤት ተጠሪዎች በቀን 06/10/2015 ዓ.ም አሻሽለዉ ባቀረቡት ክስ መሰረት ዉሳኔ የሰጠ ሲሆን ተጠሪዎች በዚህ በተሻሻለ ክሳቸው ላይ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎቸች የትርፍ ሰአት ክፍያ በማለት ሲጠይቁ በቀን በሳምንት ወይም በአመት ምን ያክል የትርፍ ሰአት ስራ እንደሰሩና ስለመስራታቸው የሚያሳይ ምንም አይነት የሰውም ሆነ የሰነድ ማስረጃ ሳያቀርቡ ፍ/ቤቱም ይህንን የማስረዳት ሸክማቸውን እንዲወጡ ሳያደርግ እንዲሁም ፍ/ቤቱ ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ በሚረዳ መልኩ ማስረጃ ሳይመዝን እንዴት አድርጎ ሂሳቡን እንደሰራው በማይታወቅ ሁኔታ የሁለት አመት የትርፍ ሰአት ክፍያ መወሰኑ እና የዓመት እረፍትን በተመለከተም በማስረጃ ሳያረጋግጡ የሰጠዉ ዉሳኔ የህግ መሰረት የሌለዉ እና ተከሳሽ በሌለበት ጉዳዩ በሚታይበት ጊዜ በከሳሽ የቀረቡትን ማስረጃዎችን የማስተባበል እድል ከሚያጣ በስተቀር ከሳሽ ወገን ማስረጃ ሳያቀርብ ሊወሰንለት የሚችልበት እድል የሌለ በመሆኑ በዚህ ረገድ የተሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡ እንዲሁም 3ኛ ተጠሪ በተሻሻለዉ ክስ ላይ የትርፍ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ሰአት ክፍያ ዳኝነት ያልጠየቁ ሆኖ ሳለ ብር 151,926.6 የትርፍ ሰአት ክፍያ በማለት መወሰኑ ባልተጠየቀ ዳኝነት ላይ የተሰጠ ነው፡፡

በመሆኑም አመልካች በሌለሁበት የተሰጠው ፍርድ ተነስቶ በጉዳዩ ገብቼ እንድከራከር ብይን እንዲሰጥልኝ፤ በሌለሁበት የተሰጠው ፍርድ እንዲነሳ የተሰጠው ብይን ሊነሳ አይገባም የሚባልበት ህጋዊ ምክንያት ቢኖር ግን ምንም አይነት ማስረጃ ሳይመዘገብና እና ባልተጠየቀ ዳኝነት ላይ የተሰጠዉ ዉሳኔ የማስረጃ ድጋፍ የለዉም ተብሎ ይሻርልኝ በማለት የሰበር ቅሬታዉን አቅርቧል፡፡

የሰበር ቅሬታው ተመርምሮ ለተጠሪዎች ለእያንዳንዳቸዉ የሁለት አመት የትርፍ ሰአት ክፍያ እንዲከፈል የተወሰነዉ በህጉ አግባብ እና በተጠሪዎች ማስረጃ ተረጋግጦ መሆን አለመሆኑን አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ጉዳዩ ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀርቡ ታዞ ተጠሪዎች ሐምሌ 24 ቀን 2016ዓ/ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡

የመልሱ ይዘት ባጭሩ አመልካች የመጀመሪያውም ይሁን የተሻሻለው ክስ እንዲደርሰውና ክሱን እንዲከካል መጥሪያ ለተከታታይ 3 ጊዜ ተልኮለታል፤ ተጠሪዎችም 3 ጊዜ መጥሪያ አድርሰን አመልካች መጥሪያውን ለመቀበል ፈቃደኛ ያለመሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት በስነስርአቱ መሰረት አመልካች መጥርያ ለመቀበል ፍቃደኛ አለመሆኑን አረጋግጦ ጉዳዩን በሌለበት አይቶ መወሰኑ ስህተት የለበትም፡፡ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 234 መሰረት አንድ ተከሣሽ ክርክሩን ክዶ ባለተከራከረበት ወይም በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 235 መሰረት በመሸሽ ካስተባበል እንዳመነ እንደሚቆጠር የሚደነግግ በመሆኑ አመልካች መጥሪያ ተልኮለት ክርክሩን ማካሄድ ካልፈገ በክሱ ላይ የቀረበውን የዳኝነት ጥያቄ እንዳመነ የሚያስቆጥር በመሆኑ በታመነ ጉዳይም ላይ ፍርድ ቤት ማስረጃ ሳይሰማ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 242 መሰረት ውሳኔ መስጠት እንደሚችል የሚደነግግ በመሆኑ ተጠሪዎች የመስረዳት ግዴታ የሚኖርብን አመልካች ቀርቦ በካደው ጉዳይ ላይ በመሆኑ እና በግልጽ ያልተካደ ጉዳይ ላይ ማስረጃ መስማት የፍታብሄር ስነስርአት ህጉ ዓላማ ባለመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች ያሳለፉት ውሳኔ በህግ አግባብ አልተወሰነም ሊባል የሚችልበት ምክንያት የለም፡፡ ስለሆነም የአመልካች ቅሬታ ዉድቅ ሆኖ የስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ በማቅረብ ቅሬታዉን አጠናክሯል፡፡

ከፍ ሲል በአጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ነው፡፡ በበኩላችን የግራ ቀኙን ክርክር ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ የተፈጸመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 78/1/ እንደተመለከተው አንድ ተከሳሽ በክርክሩ ላይ ቀርቦ መልስ ሳይሰጥ ወይም ተገቢውን መከራከሪያ ሳያቀርብ በመቅረቱ በሌለበት ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ የተሰጠ ከሆነ ውሳኔው እንዲነሳለት የማመልከት መብት እንዳለው ተደንግጓል፡፡ የዚሁ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 2 ደግሞ ተከሳሽ

የጥሪው ትዕዛዝ በሚገባ ያልደረሰው መሆኑን ወይም ክርክሩ ሊሰማ በተቀጠረበት ቀን ቀርቦ መከራከሪያውን ያላሰማ ወይም መልስ ያልሰጠው በበቂ ምክንያት መሆኑን ለፍርድ ቤቱ ያስረዳ እንደሆነ ተከሳሹ በሌለበት እንዲታይ የተሰጠው ብይን ወይም ትዕዛዙ እንደሚነሳለትና ክርክሩ እንደገና እንደሚሰማ ይደነግጋል፡፡

ከእነዚህ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 78 ንዑሳን ዴንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለው ተከሳሽ በቀነ ቀጠሮ ያልቀረበው በበቂ ምክንያት መሆኑን ፍርድ ቤቱ ከተረዳው ተከሳሹ በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ የተሰጠውን ትዕዛዝ ወይም ብይን በማንሳት ክርክሩ ተከሳሹ ባለበት እንዲቀጥል ማድረግ ያለበት ስለመሆኑ ነው፡፡ ይህ የሆነበት መሰረታዊ ዓላማም የተከሳሹን የመከራከር መብት ለመጠበቅ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ መብት መጥሪያው በህጉ አግባብ ደርሷቸው መከሰሳቸውን ያውቁ እና በቂ የሚባል ምክንያት ሳይኖራቸው ቀርበው ያልተከራከሩ ተከሳሾች ጉዳዩ በሌሉበት ታይቶ የሚሰጥ ውሳኔን ቀሪ ለማስደረግ እንዲጠቀሙበት እድል የሚሰጥ አይደለም፡፡ ስለሆነም ተከሳሽ በሌለበት የተሰጠውን ውሳኔ ለማስነሳት የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት ከማግኘቱ ወይም ውድቅ ከመደረጉ በፊት አቤቱታው በቅን ልቦና የቀረበና ከነገሩ አጠቃላይ ሁኔታ አንፃር በበቂ ምክንያት የተደገፈ መሆኑን በጥንቃቄ መመርመር ይገባል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች መጥሪያው በህጉ አግባብ አልደረሰኝም የሚል ክርክር የሚያቀርብ ቢሆንም የስር ፍርድ ቤት በዚሁ ጭብጥ ላይ ግራቀኙን ካከራከረ እና ማስረጃ ከሰማ በኃላ አመልካች የፍርድ ቤቱ መጥርያ በአግባቡ የደረሰው መሆኑን፤ ለ3 ግዜ ያህል መጥረያ አልቀበልም እያለ ምክንያት እየፈጠረ መመለሱ በማስረጃ መረጋገጡን፤ እንዲሁም አመልካች መከሰሱን አዉቆ መልስ ለመስጠት አለመፈለጉን በማረጋገጥ ወስኗል፡፡ ይህ የፍሬ ነገር መደምደሚያ በይግባኝ ሰሚው ችሎትም ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ በሰበር መ/ቁ 35403፣ 53113 እና 137704 ላይ ከተሰጡ ውሳኔዎች መገንዘብ እንደሚቻለው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 78 መሰረት የቀረበ አቤቱታ ተቀባይነት የሚያገኘው ተከሳሽ ቀርቦ ያልተከራከረው መጥሪያ ሳይደርሰው መሆኑ ከተረጋገጠ ወይም በችሎት ሳይቀርብ የቀረው በቂ በሆነ ምክንያት መሆኑ በማስረጃዎች ማረጋገጥ ሲቻል ብቻ ነው፡፡

ስለሆነም ለአመልካች መጥሪያ የደረሰው መሆኑ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ በመሆኑና በተደረገለት ጥሪ መሰረት ቀርቦ ያልተከራከረው በበቂ ምክንያት ነው የሚሰኝ ባለመሆኑ አመልካች በሌለበት የተሰጠው ውሳኔ እንዲነሳለትና ክርክሩ እንደገና እንዲታይ ያቀረበው አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውድቅ መደረጉ የስነ ስርዓት ህጉን አንቀጽ 78 ድንጋጌ ይዘትና አላማ እንዲሁም በሰበር ችሎቱ የተሰጡትን ውሳኔዎች መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በቀር የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚባል አይደለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡

በሌላ በኩል ጉዳዩ ተከሳሽ በሌለበት የሚታይ ቢሆን እንኳ ከሳሾች ያቀረቡትን ክስ በማስረጃ የማስረዳት ሸክማቸው ቀሪ ሊሆን የሚችልበት የህግ አግባብ የለም፡፡ በዚህ ረገድ የአሁን ተጠሪዎች አመልካች መጥሪያ ተልኮለት ክርክሩን ማካሄድ ካልፈገ በክሱ ላይ የቀረበውን የዳኝነት ጥያቄ አንዳመነ

ይቆጠራል፤ በታመነ ጉዳይ ላይ ፍርድ ቤት ማስረጃ ሊሰማ አይገባም፤ ተጠሪዎች የመስረዳት ግዴታ የሚኖርብን አመልካች ቀርቦ በካደው ጉዳይ ላይ ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር የፍታብሄር ስነስርአት ህጉን ይዘት የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

የስር ፍርድ ቤት በተለይ የትርፍ ሰዓት ክፍያ እንዲከፈል ሲወስን የተጠሪዎች ክርክር ከመታየቱ በቀር በጉዳዩ ላይ ማስረጃ መስማቱን መዝገቡ አያሳይም፡፡ በተጠሪዎች ማስረጃ ወይም አግባብ ባለው ማስረጃ ሁሉ እንዲጣራ ሳይደርግ የሚሰጥ ውሳኔ ደግሞ የሥነ ሥርዓት ህጉን የተከተለ አይሆንም፡፡ ተገቢው ውሳኔ ላይ ለመድረስ ጥረት ሳይደረግ የአሁን ተጠሪዎች ያቀረቡትን ብቻ መሰረት በማድረግ የተሰጠው ውሳኔ ተቀባይነት የለውም፡፡

ስለሆነም ተጠሪዎች ያቀረቡት ክርክር በአግባቡ ታይቶና ተገቢው ትኃት ተደርጎበት በማስረጃ እንዲጣራ ተደርጎ በዝርዝር ምክንያት የተደገፈ ውሳኔ ሊሰጥ ሲገባ በዚህ አግባብ ሳይታይ፣ ሳይጣራና በአግባቡ ሳይመረመር የሁለት አመት የትርፍ ሰዓት ክፍያ እንዲከፈል የተሰጠው ውሳኔ የህግ መሰረት ያለው ባለመሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች በየደረጃው የተሰጠው ውሳኔ በዚህ ረገድ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 152224 ሀምሌ 13 ቀን 2015 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና ህዳር 25/2016 ዓ.ም ያሳለፈው ብይን፤ እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 316062 ታህሳስ 24 ቀን 2016 ዓ/ም ይግባኙን በመሰረዝ የሰጠዉ ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2. ለአመልካች መጥሪያ የደረሰው መሆኑ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ በመሆኑና በተደረገለት ጥሪ መሰረት ቀርቦ ያልተከራከረው በበቂ ምክንያት ነው የሚሰኝ ባለመሆኑ አመልካች በሌለበት የተሰጠው ውሳኔ እንዲነሳለትና ክርክሩ እንደገና እንዲታይ ያቀረበው አቤቱታ ውድቅ መደረጉ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡

3. በማስረጃ ሳይጣራ ለተጠሪዎች የሁለት አመት የትርፍ ሰዓት ክፍያ እንዲከፈላቸው የተሰጠው ውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡

4. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ ተጠሪዎች ካቀረቡት ክርክርና በተገቢው ማስረጃ ሁሉ በማጣራት የትርፍ ሰዓት ክፍያን በተመለከተ በዝርዝር በምክንያት የተደገፈ ውሳኔ እንዲሰጥ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 343(1) መሰረት ጉዳዩን መልሰናል፡፡ የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይድረሰው፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማ አያገለግልም!

5. ሌላው የውሳኔ ክፍል የፀና ነው፡፡
6. የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
7. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

ውሳኔው ታህሳስ 2/2017 ዓ.ም ተነቧል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

**የሰ/መ/ቁ** 257602

**ህዳር** 24 **ቀን** 2017**ዓ/ም**

**ዳኞች፡-** ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ብርቅነሽ እሱባለው

ሀብታሙ እርቅይሁን

**አመልካች** - አብይ ምክረስላሴ

**ተጠሪ** - ይበሉመሰዋ የደረቅ ፈሳሽ ጭነት ማመላለሻ የግል ትራንስፖርት

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ጉዳዩ የግል የሥራ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን፣ ክርክሩ በተጀመረበት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ባቀረቡት ክስ ከታህሳስ 27 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ በተጠሪ ድርጅት ተቀጥሮ በወር ብር 31897.00 ደመወዝ እየተከፈላቸዉ የጋራዥና ቴክኒክ ክፍል በመሆን በመስራት ላይ እያሉ ተጠሪ ከህግ ዉጪ የስራ መደብ ለዉጥ በማድረግ ከጥቅምት 17 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ በወር ብር 21721.00 ደመወዝ እየተከፈላቸዉ የጥገና የጥገና ክፍል ከፍተኛ መካኒክ እንዲሰራ ምደባ የሰጣቸዉ መሆኑን ጠቅሰዉ ያላግባብ የተቀነሰባቸዉ ደመወዝ ወደ ነበረበት እንዲመለስ፣ ወደ ነበሩበት የስራ መደብ እንዲመለሱ ይወሰንላቸዉ ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ ለክሱ በሰጠዉ መልስ አመልካች የስራ መሪ ናቸዉ የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማስቀደም ስንብቱ ህጋዊ ነዉ የሚልባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር ክሱ ዉድቅ ሆኖ ይወሰንለት ዘንድ ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች በህጉ አግባብ የስራ መሪ መሆናቸዉን የሚያሳይ ማስረጃ በክርክሩ መሠረት ተጠሪ ያላቀረበ መሆኑን ጠቅሶ ተጠሪ በዚህ ረገድ ያቀረበዉን መቃወሚያ ዉድቅ በማድረግ የፍሬ ነገር ክርክሩን መርምሮ ተጠሪ አመልካችን አስመልክቶ የስራ መደብ ለዉጥ ያደረገበት አግባብ ከህግ ዉጪ ነዉ የሚልባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር ተጠሪ አመልካች ወደ ነበሩበት የስራ መደብ እንዲመልስና በስራ መደብ ለዉጥ ምክንያት የተፈጠረዉን የደመወዝ ልዩነትም እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪ በዚህ ዉሳኔ ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን፣ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ በበኩሉ የይግባኝ አቤቱታዉን አስቀርቦ ከመረመረ በኋላ አመልካች በተጠሪ ድርጅት ሠራተኛን የማዘዋወር ወይም የመመደብ ስልጣን ያላቸዉ ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ደምድሞ አመልካች ሠራተኛን የመቅጠርና የማሰናበት ስልጣን የላቸዉም በሚል የሰጠዉ ዉሳኔ ሠራተኛን የመመደብ እና የማዛወር ስልጣን ያለዉ ያለዉ ሠራተኛ የስራ መሪ እንደሚሰኝ በአዋጁ አንቀጽ 2(10) ስር የተመለከተዉን ድንጋጌ ያገናዘበ አለመሆኑን ጠቅሶ የስር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካች ጥር 07 ቀን 2016 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ አመልካች በተጠሪ ድርጅት ዉስጥ ሠራተኛን የመቅጠር፣ የማሰናበት፣ የመመደብም ሆነ የማዛወር ስራ እንደማይሰሩ እና ይህን ስራ መስራታቸዉን የሚያሳይ ማስረጃ ተጠሪ አለማቅረቡን ጠቅሶ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዉሳኔ ተሽሮ የስር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዉሳኔ ጸንቶ እንዲወሰንላቸዉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የሰበር አቤቱታዉ በሰበር ችሎት ተመርምሮ ያስቀርባል በመባሉም ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ ጥሪ ተደርጎለታል፡፡ በዚህም መሠረት ተጠሪ ግንቦት 09 ቀን 2016 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች የስራ መሪ መሆናቸዉ ተረጋግጦ በተሰጠ ዉሳኔ ላይ የተፈጸመ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም የሚልባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር ጸንቶ እንዲወሰንለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡ አመልካች ግንቦት 15 ቀን 2016 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል፣ ይህ ችሎትም በስር ፍርድ ቤት በተሰጠ ዉሳኔ ላይ የተፈጸመ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡

እንደመረመረዉም በአሠሪና ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 2(10) ላይ እንተመለከተዉ አንድ ሠራተኛ የስራ መሪ ነዉ ለማለት ከሌሎች በህግ ወይም እንደ ድርጅቱ የስራ ጠባይ በአሠሪዉ በተሰጠዉ የዉክልና ስልጣን መሠረት የስራ አመራር ፖሊሲዎችን የማዉጣትና የማስፈጸም ስልጣን ያለዉ ወይም ሠራተኛን የመቅጠር፣ የማዘዋወር፣ የማገድ፣ የማሰናበት ወይም የመመደብ ተግባሮችን ለማከናወን ስልጣን ያለዉ ሰዉ እንደሆነ ይደነግጋል፡፡ በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች የሠራተኛ ምደባ እና ዝዉዉር የሚፈጽሙ ስለመሆኑ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ የስር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይህን የፍሬ ነገር ድምዳሜ ተቀብሎ ሲያበቃ አመልካች የስራ መሪ አይደሉም በሚል ለሰጠዉ ዉሳኔ መሠረት ያደረገዉ

አመልካች ዕቅድ እንደማያወጡ እና በራሳቸዉም የሚፈጽሙ ስለመሆኑ ተጠሪ አለማስረዳቱን እንዲሁም ሠራተኛን የማይቀጥሩ እና የማያሰናብቱ በመሆኑም የስራ መሪ ሊባሉ አይችሉም የሚል ይዘት ያለዉ ምክንያት በመጥቀስ ስለመሆኑ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል አንድን ሠራተኛ የስራ መሪ የሚያሰኙት ተግባራትን አስመልክቶ በአዋጁ አንቀጽ 2(10) ላይ ከተዘረዘሩት ዉስጥ ቢያንስ አንዱን የማከናወን ስልጣን ያለዉ ሠራተኛ የስራ መሪ ሊባል እንደሚችል ከድንጋጌዉ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም አመልካች ምንም እንኳ ሠራተኞችን የመቅጠርና የማሰናበት እንዲሁም ዕቅድ የማዘጋጀት እና የማስፈጸም ተግባራትን የሚያከናዉን ስለመሆኑ ባይረጋገጥም የሠራተኞችን ምደባ እና የዝዉዉር ሥራን እንደሚያከናዉኑ ተረጋግጧል፡፡

በሌላ በኩል በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ መንግስት እና ህገ መንግስቱን መሰረት አድርጎ በወጣው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሰረት ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው የዳኝነት ሥልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸውን ማናቸውንም የመጨረሻ ዉሳኔዎችን መርምሮ ማረም ስለመሆኑ የህገ መንግስቱ አንቀጽ 80(3/ሀ)) እና የአዋጁ አንቀፅ 10 ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት እንደሆነ በአዋጁ የትርጉም ክፍል በአንቀጽ 2(4) ስር በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ በዚህ መሠረት አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ተብሎ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችለዉ ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ ዉሳኔ በአዋጁ አንቀጽ 2(4) ስር ከተመለከቱት ሁኔታዎች ዉስጥ ቢያንስ አንዱን የሚያሟላ ሆኖ ዉጤቱም ፍትሕን የሚያዛባ ጉልህ ስህተት ያለበት ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ ከድንጋጌዎቹ አጠቃላይ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

ከዚህ ሁሉ አንፃር ሲታይ አመልካች ሠራተኞችን የመመደብ እና የማዘዋወር ስልጣን ያለዉ መሆኑ ተረጋግጦ ባለበት ሁኔታ አንድን ሠራተኛ የስራ መሪ የሚያሰኙ በአዋጁ የተመለከቱትን ሌሎች ቀሪ ተግባራትን አመልካች የማያከናዉኑ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም በሚል አመልካች የስራ መሪ አይደሉም በሚል የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ በርግጥም ከላይ የተመለከተዉን የአዋጁን ድንጋጌ ትክክለኛ ይዘት ያላገናዘበ በመሆኑ፣ ይህን በማረም በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተሰጠ ዉሳኔ ላይ የተፈጸመ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ዉሳኔ**

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 307478 ላይ ጥቅምት 07 ቀን 2016 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ በሰበር ሥ/ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1) መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ዉሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

*የሰ/መ/ቁ 257998*
*ህዳር 25 ቀን 2017ዓ/ም*

ዳኞች፡ ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ብርቅነሽ እሱባለው

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች፡ ካፕቴን ሲዶኔ ኬቭን ሁበርት ጆርጅስ - ጠበቃ ግሩምነህ ግዛው - ቀረቡ

ተጠሪ፡ የኢትዮጵያ አየር መንገድ - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍርድ</u>

ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ የቀረበው አመልካች የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት በመዝገብ ቁጥር 150714 በ20/10/2015ዓ.ም በሰጠው ብይን እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት በመዝገብ ቁጥር 310394 በ27/3/2016ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት በ14/5/2016ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አመልካች በስር የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ተጠሪ አመልካችን በኢ.ሲ. ኤክስፓት ፓይለት በውጭ ዜጋ አብራሪነት በ22/1/2011ዓ.ም በተፈረመ የስራ ቅጥር ውል ለተወሰነ ግዜ የቀጠረ ሲሆን በ26/2/2011ዓ.ም በተጻፈ ግዜያዊ የቅጥር ደብዳቤ

ደግሞ የአመልካች ወርሃዊ ደመወዝ የአሜሪካን ዶላር 9000(ዘጠኝ ሺ.ህ) እንደሚሆን አረጋግጦለታል፡፡ ከኮቪድ ወረርሽኝ ጋር በተያያዘ ተጠሪ አመልካችን ከየካቲት 20 ቀን 2012ዓ.ም ጀምሮ ክፍያ በሌለው እረፍት ላይ እንዲቆይ የወሰነ ሲሆን ወረርሽኙ ጋብ ካለ በኋላ በህዳር ወር 2014ዓ.ም ስራውን የሚቀጥልበትን ሁኔታ ለመነጋገር አመልካች አዲስአበባ በመጣበት ወቅት ከበረራ ስራ ክፍል የሰው ሀይል ሃላፊ ከሆኑት ከአቶ ምህረቱ ቦርሳሞ የተነገረው ክፍያ በሌለው እረፍት ላይ እንዲቆይ ከተወሰነበት ግዜ ጀምሮ ከአመልካች ጋር ያለው የስራ ግንኙነት የተቋረጠ መሆኑን በመሆኑ አመልካች በስራው የማይቀጥል ከሆነ ለስልጠና ሲባል ተጠሪ የያዘበትንና ተመላሽ ሊያደርግለት የሚገባውን ዩኤስዲ 15,000 ተመላሽ እንዲደረግለት ጠይቋል፡፡

ሃላፊውም ህዳር 13 ቀን 2014ዓ.ም በአመልካች የኢሜይል አድራሻ በተጻፈ አመልካች ያለውን የገንዘብ ይመለስልኝ ጥያቄ ወደህግ ካላመራው ለሁለቱም በሚጠቅም ሁኔታ ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት ሃሳቡን እንዲሰጣቸው በጠየቁት መሰረት በዚያው ቀን በኢሜይል አድራሻቸው በላከላቸው መልእክት በሃሳባቸው መስማማቱን አስታውቆ በሳምንት ግዜ ውስጥ መፍትሄ እንዲሰጡት አስታውቋቸዋል፡፡ ሆኖም አመልካች መልስ ሳያገኝ ከሰባት ወራት በላይ በመቆየቱ የአመልካች የህግ አማካሪ ሰኔ 22 ቀን 2014ዓ.ም በተጻፈ የኢሜይል ደብዳቤ ህጋዊ ማስጠንቀቂያ በመስጠት በአስር የስራ ቀናት ውስጥ መፍትሄ የማያገኝ ቢሆን ጉዳዩን ወደፍርድቤት የሚያመራው ስለመሆኑ አስጠንቅቆታል፡፡ ተጠሪ ለዚሁ ደብዳቤ ሀምሌ 7 ቀን 2014ዓ.ም በተጻፈ ለአመልካች በሰጠው ምላሽ ተጠሪ ባለው የስራ መርህና ደንብ መሰረት ካፕቴኑን መልሶ ለመቅጠር የወሰነ መሆኑንና በዚህ አግባብ የቅጥርና የምደባ ቢሮ ካፒቴኑን በአጭር ግዜ ውስጥ የሚያገኝ እና የሚያነጋግር መሆኑን ገልጿል፡፡ ሆኖም ተጠሪ ለአመልካች ያቀረበለት አዲስ ሀሳብ የቅጥር ውሉን ከመፈጸምህ በፊት በድርጅቱ ላይ ያለህንን ወደፊትም ሊኖርህ የሚችልን ማናቸውንም የይገባኛል ጥያቄ ላለማንሳት የእርቅ ወይም የመተው ስምምነት ማድረግ አለብህ የሚልና ለዚህም መስከረም 26 ቀን 2015ዓ.ም የተረቀቀ ሰነድ ማቅረብ ነበር፡፡

አመልካች ከተጠሪ የቀረበለትን መብቱን ሊያሳጣ የሚችል ህገወጥ ስምምነት ስራውን ላለማጣት ሲል መስከረም 26 ቀን 2015ዓ.ም የተረቀቀውን ሰነድ በመቀበል የድርሻውን ፈርሞ ለተጠሪ ቢሰጥም ተጠሪን ግን የስራ ውሉን አቋረጥኩኝ እስካለበት እስከ ህዳር 14 ቀን 2015ዓ.ም ድረስ ፈርሞ ሳይሰጥ በመቅረት የአመልካችን የስራ ውል ከህግ ውጪ አቋርጦታል፡፡ ተጠሪ የአመልካችን የስራ ውል ለማቋረጥ የሰጠው ምክንያት በበረራ ኦፕሬሽን ማኑዋል መሰረት አሁናዊ ስልጠና መውሰድ ያለበት በመሆኑና እርሶም ይህን ስልጠና ወስደው ሲገመገሙ በስልጠናው ወቅት በቂ

እድል የተሰጠዎት ቢሆንም የሚፈለገውን አፈጻጸም ማሳየት ባለመቻልዎና መሻሻልም ባለማሳየትዎና ለበረራ በቂ ሆነው ባለመገኘትዎ በኩባንያው እና በርስዎ መካከል በ22/1/2011ዓ.ም በተፈረመው የስራ ውል አንቀጽ 7(2)፣7(2)(2) እና 7(2)(10) መሰረት የስራ ውልዎ ያለማስጠንቀቂያ ተቋርጧል የሚል ነው፡፡ ሆኖም ተጠሪ አመልካችን የተባለውን ስልጠና እንዲወስድ መቼ እንዳስታወቀው፣ ስልጠናውን የት መውሰድ እንዳለበት፣የስልጠናውን የግዜ ርዝመት፣ ስልጠናውን እንዲወስድ በምን ሁኔታ እንዳስታወቀው ሳያብራራና ሳይገልጽ መቅረቱ የሚያመለክተው ይህን አይነት ስልጠና እንዲወስድ ተጠሪ ያላዘዘው መሆኑን፣ ይህ ስልጠና አመልካች በወቅቱ ለያዘው የስራ መደብ የማይሰጥ መሆኑን ነው፡፡ አመልካች ከያዘው የስራ መደብ አንጻር መውሰድ የሚገባው አሁናዊ ስልጠና(recurrent training) ሳይሆን የዳግም መብቂያ (requalification training) መሆኑን ከተጠሪ የበረራ ስራ (flight operation) የዳግም ማብቂያ/ሙሉ መሸጋገሪያ ኮርስ (Requalification/Full Transition Course as per the FLIGHT OPERATIONS TRAINING PROGRAM MANUAL(FOTPM) መሆኑን ተጠሪ በመገንዘብ ተጠሪ ይህን ስልጠና እንዲወስድ ባስታወቀው መሰረት ይህን ስልጠና ወሰደ እንጂ አሁናዊ ስልጠና እንዲወስድ አልታዘዘም፡፡ ምክንያቱም አሁናዊ ስልጠና በማብረር ስራ ለተሰማራ አብራሪ በየስድስት ወራቱ የሚሰጥ በመሆኑና የዳግም ማብቂያ ስልጠና የሚሰጠው ግን ከሁለትና ከዚያ በላይ ለሆኑ አመታት ከበረራ ስራ ተገልለው ለቆዩ አብራሪዎች ነው፡፡ ስለሆነም ተጠሪ አመልካች እንዲወስድ ያላዘዘውን ስልጠና እንደወሰደ አድርጎ ደርሼበታለሁ በሚለው የግምገማ ውጤት መሰረት የስራ ውሉን ማቋረጡ ህጋዊ አይደለም፡፡

ስለሆነም ተጠሪ አመልካች ያለውን ህጋዊ መብት እንዲተው ያስፈረመው የመስከረም 26 ቀን 2015ዓ.ም የእርቅ ስምምነት በህግ ፊት የሚጸና አይደለም እንዲባልና፣ ከዚህ ውል በፊት ተጠሪ ለአመልካች ሊመልስለት ይገባ የነበረውን ለስልጠና ያስያዘውን 15,000 የአሜሪካን ዶላር ከ26/1/2015ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር ለአመልካች እንዲከፍል እንዲወሰንበት፣ አመልካች እንዲወስድ ባልታዘዘውና ባልወሰደው ስልጠና ተገምግሞ ማሻሻል አላሰየምና ለበረራ ብቁ አልሆነም ተብሎ የስራ ውሉ መቋረጡ ከህግ ውጪ ነው እንዲባል፣ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 43(4)(ለ) መሰረት የአመልካችን አማካይ የቀን ደመወዝ(300 የአሜሪካን ዶላር) በ180 ተባዝቶ 54,000 የአሜሪካን ዶላር ሊከፍል ይገባው ከነበረበት ከ15/3/2015ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍል እንዲወሰንበት፣ ክፍያ ለዘገየበት የሶስት ወራት ደመወዝ 27,000 የአሜሪካን ዶላር ከ21/3/2015ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ

ጋር ወጪና ኪሳራን ጨምሮ እንዲከፍል እንዲወሰንበት በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎችንም አቅርበዋል፡፡

ተጠሪ ባቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የፍሬጉዳይ መልስ አመልካች ለስልጠና አስያዝኩት የሚሉት 15,000 የአሜሪካን ዶላር ከመጀመሪያው የስራ ውላቸው ጋር የተገናኘ ነው፡፡ አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበራቸው የመጀመሪያ የስራ ውል ከመጋቢት 12 ቀን 2012ዓ.ም ጀምሮ ተቋርጧል፡፡ ስለሆነም ከዚህ ጋር የተገናኘ ማንኛውንም የክፍያ ጥያቄ በስድስት ወር ውስጥ ማቅረብ ሲገባው ያላቀረቡ በመሆኑ ከዚህ ጋር ተያይዞ ያቀረቡት ክስ በአሰሪና አራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 163(3) መሰረት በይርጋ ቀሪ ነው፡፡ አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበራቸው የመጀመሪያ የስራ ውል በ12/7/2012ዓ.ም ከተቃረጠ በኋላ ለስልጠና ያስያዙትን 15,000 የአሜሪካን ዶላር እንዲመልስላቸው የጠየቁ ሲሆን በ22/10/2014ዓ.ም በተጠሪ አለኝ የሚሉት ገንዘብ እንዲመለስላቸው አመልካች በጠበቃቸው በኩል የህግ ማስጠንቀቂያ ሰጥተዋል፡፡ ሆኖም ተጠሪ ይህ በአመልካች የተጠየቀው ገንዘብ ሊመለስ አይገባም የሚል አቋም ስለነበረው በሁለቱም ወገኖች አለመግባባት ተፈጥሮ ነበር፡፡ አመልካች ከክሱ ጋር አያይዘው ባቀረቡት በ22/1/2011ዓ.ም በተደረገው የስራ ውል አንቀጽ 3 እና 5 መሰረት አመልካች ከስልጠናው መጠናቀቅ በኋላ ተጠሪን ለተከታታይ 3 አመታት ለማገልገል የተስማሙ ሲሆን ይህ የማገልገል ግዴታቸውን ካልተወጡ ያስያዙት ገንዘብ የማይመለስ ስለመሆኑ ተደንግጓል፡፡

አመልካች በኮቪድ ምክንያት እረፍት ከወጡ በኋላ ተመልሰው በገቡት ውል መሰረት ተጠሪን ማገልገል የነበረባቸው ቢሆንም ወደስራቸው ሳይመለሱ በመቅረታቸው በራሳቸው በሆነ ምክንያት ከድርጅቱ እንዲሰናበቱ ተደርጓል፡፡ ከዚህ በኋላ አመልካች ወደስራ እንዲመለሱ የጠየቁ ሲሆን ተጠሪም ወደስራቸው በግዜው ያልተመለሱ በመሆኑ የስራ ውላቸው የተቋረጠ መሆኑን ካሳወቀቸው በኋላ ለስልጠና ተብሎ ያስያዙትን ገንዘብ እንዲመልስላቸው ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪ አመልካች በውሉ መሰረት ድርጅቱን ለሶስት አመታት የማገልገል ግዴታቸውን ያልተወጡ በመሆኑ ገንዘቡ አይመለስም የሚል አቋም የነበረው ሲሆን አመልካችም ወደስራ ያልተመለስኩት በኮቪድ 19 ከሀገሬ መውጣት ስለማልችል ነው በማለታቸው በሁለቱም ወገኖች መካከል አለመግባባት ተፈጥሯል፡፡ ተጠሪ የአመልካችን ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት አለመግባባታችን በስምምነት እንዲፈታ ባቀረበው ሀሳብ አመልካችም የተስማሙ በመሆኑ በ26/1/2015ዓ.ም የእርቅ ስምምነት ተፈራርሚል፡፡ ይህ የእርቅ ስምምነት የመጀመሪያ የስራ ውል (Previous Employment Contract) የተመለከተ ስለመሆኑ በስምምነቱ ላይ ሰፍሯል፡፡

አመልካች እና ተጠሪ በ26/1/2015ዓ.ም ባደረጉት የእርቅ ስምምነት አመልካች ከመጀመሪያ የስራ ውል ጋር በተገናኘ ያላቸው ማናቸውም ጥያቄ በስምምነት የተፈታ መሆኑን፤ የነበራቸው ጥያቄ በስምምነት የተመለሰላቸው መሆኑን እና ወደፊት ከዚህ የስራ ውል ጋር በተገናኘ የሚያነሱት ጥያቄ የሌለ መሆኑን እንዲሁም ተጠሪ አመልካችን መልሶ ለመቅጠር የተስማማ መሆኑን በውሉ አስቀምጧል። ይህ ስምምነትም አመልካች የሚገባቸውን መብት ለማስቀረት የተደረገ ስምምነት ሳይሆን የስራ ውሉ ላይ አመልካች እና ተጠሪ የነበራቸውን አለመግባባት እንዲፈቱ ያደረገ ነው። ስለሆነም በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የነበረውን የመጀመሪያ የስራ ውል የተመለከተውን ሁሉም አለመግባባቶች በስምምነት ያለቀ በመሆኑ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 244(2)(ረ) መሰረት ክሱ ውድቅ እንዲደረግ።

አመልካች 2ኛው የስራ ውሌ በህገወጥ መንገድ ተቋርጦብኛል ሲሉ ያቀረቡትን ክርክር በተመለከተ አንድ ስራ ላይ ያልነበረ ካፕቴን የበረራ ስራ እንዲሰራ እና ተመልሶ እንዲቀጠር ድርጅቱ የሚሰጠው ዓለምአቀፍ መመዘኛውን የሚያሟላ እና የሀገሪቱ አቪዬሽን ስራ በሚቆጣጠር የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለስልጣን የጸደቀውን ስልጠና ወስደው ብቁ ሆነው መገኘት አለባቸው። አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበራቸው የመጀመሪያ የስራ ውል መጋቢት 12 ቀን 2012ዓ.ም የተቋረጠ መሆኑ የተካደ ጉዳይ አይደለም። አመልካች የስራ ውላቸው ከተቋረጠ በኋላ ከሁለት አመት በላይ ስራ ያልሰሩ በመሆኑ በድርጅቱ ውስጥ ስራ እንዲቀጠሩ ስልጠና ወስደው ፈተናውን ማለፍ አለባቸው።

በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በተደረገው ስምምነት መሰረት ተጠሪ አመልካችን መልሶ ለመቅጠር የተስማማው የስምምነቱ አካል እንዲሆን በአባሪነት ተያይዞ በነበረው የስራ ውል ውስጥ በተደነገጉ ሁኔታዎች እና ደንቦች መሰረት ነው። በዚህ መሰረት መስከረም 26 ቀን 2015ዓ.ም በተፈረመው የስምምነቱ አባሪ እና አካል ተደርጎ በነበረው የስራ ውል አንቀጽ 1(2) መሰረት በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የስራ ውል ሊኖር የሚችለው አመልካች የሚሰጣቸውን ስልጠና በተሳካ ሁኔታ ሲያጠናቅቁ እና የተሰጣቸውን ፈተና ማለፍ መቻላቸውን ተከትሎ ተጠሪ የቅጥር ደብዳቤ ሲሰጣቸው ብቻ መሆኑን ተቀምጧል። በተጨማሪም በዚህ አንቀጽ ላይ አመልካች ስራ የሚጀምሩበትን ግዜ የሚገልጽ የቅጥር ደብዳቤ ካልተሰጣቸው በስተቀር በሁለቱም ወገን ምንም አይነት የስራ ውል የሌለ መሆኑ ተደንግጓል። በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተደረገው የስራ ውል ተፈጻሚ የሚሆነው ውሉ በተፈረመበት ቀን ሳይሆን ወደፊት የስልጠናው ውጤት ታይቶ ነው። አመልካች ካፕቴን እንደመሆናቸው መጠን በድርጅቱ ፖሊሲ እና በኢትዮጵያ ሲቪል

አቪዬሽን ባለስልጣን መመሪያ መሰረት ስራ እንዲቀጠሩ በመመሪያው የተገለጸውን ዝቅተኛ መስፈርት ማሟላት አለባቸው፡፡

አመልካች በድርጅቱ የስልጠና መመሪያ መሰረት መውሰድ ያለባቸው የማብቂያ ስልጠና (requalification training) መሆኑን፤ ተጠሪ ይህን በመገንዘብ የማብቂያ ስልጠና እንዲወስዱ በጽሁፍ ባስታወቀው መሰረት የማብቂያ ስልጠና ወስደው ስልጠናውን ማለፍ ባለመቻላቸው እና ለስራ ብቁ ሆነው ባለመገኘታቸው ስራ ሳይቀጠሩ ከተጠሪ ጋር የነበራቸው ግንኙነት እንዲቋረጥ ተደርቋል፡፡ በመሆኑም በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በቅጥር ላይ የተመሰረተ የስራ ግንኙነት በሌለበት ሁኔታ እና ገና የቅድመ ቅጥር ስልጠና ላይ እያሉ ስልጠና ባለማለፋቸው ግንኙነታቸው የተቋረጠ በመሆኑ ክሱ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 3(1) መሰረት ውድቅ እንዲደረግ በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍርድቤቱም ክሱን ሰምቶ ጭብጦችን በመያዝ የአመልካች እና የተጠሪን ምስክሮች ከሰማ በኋላ ከሰነድ ማስረጃዎች ጋር ጉዳዩን መርምሮ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል መስከረም 22 ቀን 2011ዓ.ም የተደረገው የስራ ውል በኮቪድ 19 ምክንያት ተጠሪ ፓይለቶችን ላልተወሰነ ግዜ ያለክፍያ እረፍት በመስጠት ከስራ ውጪ ካደረጋቸው በኋላ ቫይረሱ እየቀነሰ በመምጣቱ በድጋሚ ጥሪ ሲያደርግላቸው አመልካች ጥሪውን አክብረው ወደስራ ገበታቸው ባለመመለሳቸው እኤአ የካቲት ወር 2020 የስራ ውሉ የተቋረጠ ስለመሆኑ የአመልካች እና የተጠሪ ምስክሮች አረጋግጠዋል፡፡ ይህ የስራ ውል መቋረጡን ተከትሎ አመልካች አስቀድሞ በነበራቸው የስራ ውል ወቅት ያስያዙትን 15,000 ዶላር ይመለስልኝ በማለት ተጠሪን በመጠየቃቸው ምክንያት ግራቀኙ ወደፊት በሚከሰት ሁኔታ ላይ የተመሰረተ አዲስ የስራ ቅጥር ውል መስከረም 26 ቀን 2015ዓ.ም አድርገዋል፡፡ ይህ ውል አመልካች በቦይንግ 777 እና 778 አውሮፕላን ላይ ስልጠና ወስደው ስልጠናውን በብቃት ካጠናቀቁ አዲስ የስራ ውል ለማቋቋም ሲሆን ሆኖም ስልጠናውን በብቃት ካልተወጡ የስራ ቅጥር ውሉ ውጤት እንደማይኖረው ወይም ተጠሪ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ እንደሚያቋርጥ የሚገልጽ ሲሆን ቀደም ሲል ከነበረው የስራ ውል ጋር የተያያዙ ግዴታዎች በአዲሱ የስራ ቅጥር ውል መሰረት ቀሪ ስለመሆናቸው ያመለክታል፡፡ ይህም አመልካች አሁን የጠየቁትን 15,000 ዶላር ክፍያን በአዲሱ የስራ ውል መሰረት ይከፈለኝ ብለው ላይጠይቁ እንደተዋዋሉ ያሳያል፡፡ አመልካች በውላቸው መሰረት የተሰጣቸውን ስልጠና በብቃት ማጠናቀቅ ያልቻሉ ስለመሆናቸው የአመልካች እና የተጠሪ ምስክሮች አስረድተዋል፡፡

ስለሆነም በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ጥቅምት 26 ቀን 2011ዓ.ም የተደረገው የስራ ውል የካቲት 2012ዓ.ም የተቋረጠ ሲሆን ከዚህ የስራ ውል ጋር የተያያዙ በግራቀኙ የነበሩ ግዴታዎችም መስከረም 26 ቀን 2015ዓ.ም ባደረጉት የስራ ውል ስምምነት መሰረት ቀሪ ያደረጓቸው በመሆኑ አመልካች ተጠሪን 15,000 ዶላር ክፍያ ሊጠይቅ አይገባም፤ ግራቀኙ መስከረም 26 ቀን 2015ዓ.ም ያደረጉት የስራ ውልም የተቀመጠለት የአመልካች ስልጠናውን በብቃት ተወጥቶ የማለፍ ሁኔታ ባለመሟላቱ ምክንያት ውጤት ያላገኘ በመሆኑ በግራቀኙ መካከል የስራ ውል አለ ለማለት ስለማይቻል የአመልካች ክስ የክስ ምክንያት የለውም በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ብይን ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት አቅርበው ፍርድቤቱም የተጠሪን መልስ ከተቀበለ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ በሰጠው ውሳኔ የስር ፍርድቤትን ብይን አጽንቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ከላይ የተገለጹትን ብይን እና ውሳኔ በመቃወም ሲሆን ይዘቱም አመልካች በተጠሪ ላይ ላቀረቡት ክስ ተጠሪ ባቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ብይንና ትእዛዝ ሳይሰጥ በፍርድቤቱ በተያዙ ጭብጦች ላይ ምስክሮች እንዲሰሙ አድርጎ መዝገቡን በብይን መዝጋቱ እና ይህንኑ ብይን ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት በማጽናት የሰጠው ውሳኔ የስነስርአት ህጉን ድንጋጌዎች የሚቃረን በመሆኑ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት በፍሬጉዳዩ ላይ የግራቀኙን ክርክር ሰምቶ በመሰለው እንዲወስን ጉዳዩ እንዲመለስለት የሚል ነው፡፡

የሰበር አቤቱታው በሰበር ችሎቱ እንዲታይ በሰበር አጣሪ ችሎት በመመራቱ ተመርምሮ አመልካች ከተጠሪ ጋር መስከረም 26 ቀን 2015ዓ.ም በቀደመው የስራ ውል ግንኙነት ሊከፈላቸው የሚገባ 15,000 ዶላር ለመተው እና ቅጥር ለመፈጸም ያደረጉት ስምምነት በሕግ ፊት ሊጸና አይገባም በማለት ያቀረቡትን በተመለከተ ዳኝነት ሳይሰጥ ያለፈበትን እና አመልካች በተጠሪ የተሰጣቸውን ስልጠና በብቃት ሊያልፉ ያልቻሉ በመሆኑ ክሱን ለማቅረብ መብት የላቸውም ሲል የሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ከአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 25፤ ከክርክር አመራር ስርአት እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንጻር ለመመርመር ተጠሪን ያስቀርባል በማለት በ25/7/2016ዓ.ም በተሰጠው ትእዛዝ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በ15/8/2016ዓ.ም በተጻፈ ባቀረበው መልስ የስር ፍርድቤቶች የሰጡት ብይን እና ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አልተፈጸመበትም የሚልበትን ምክንያት በመዘርዘር እንዲጸና ጠይቋል፡፡ አመልካች በ30/8/2016ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ይህ የሰበር ሰሚ ችሎትም የአመልካችን የሰበር አቤቱታ አቤቱታ ከቀረበበት ብይን እና ውሳኔ እንዲሁም ከተገቢዎቹ የህግ ድንጋጌዎች አንጻር የስር ፍርድቤቶች የሰጡት ብይን እና ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገመንግስት አንቀጽ 80(3)(ሀ) ሆነ በፌደራል ፍርድቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 እንደተደነገገው ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ስልጣን መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበትን የመጨረሻ ውሳኔ እንዲያርም ነው፡፡ አንድ ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻለው በፌደራል ፍርድቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4) ከ “ሀ-ሸ ” ከተዘረዘሩት ውስጥ ቢያንስ አንዱን የሚያሟላ ሆኖ በውጤቱም ፍትሕን የሚያዛባ ጉልህ የህግ ስህተት የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 2(4) ድንጋጌ ይዘት የሚያስገነዝብ ነው፡፡

የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 25(1) ተዋዋይ ወገኖች የስራ ውላቸውን በስምምነት ለማቋረጥ ይችላሉ፡፡ ሆኖም ሰራተኛው በህግ የተሰጠውን መብቱን ለመተው የሚያደርገው ስምምነት የህግ ውጤት አይኖረውም በማለት ደንግጓል፡፡ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 245 ድንጋጌ በፍታብሔር ክርክር የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ ሲቀርብ ፍርድቤቱ ሌላው ተከራካሪ ወገን በመቃወሚያው ላይ የሚያቀርበውን ክርክር ከሰማ በኋላ መቃወሚያውን ለመወሰን ተገቢ መስሎ የሚገምተው ማስረጃ እንዲቀርብለት ትእዛዝ እንደሚሰጥ እና በመጨረሻም የቀረበውን መቃወሚያ ከማስረጃው አንጻር መርምሮ ተገቢውን ብይን መስጠት ያለበት ስለመሆኑ ያስገነዝባል፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች በስር ክሳቸው እንዲመለስላቸው የጠየቁት ለስልጠና ያስያዙት 15,000 የአሜሪካን ዶላር ጥቅምት 26 ቀን 2011ዓ.ም ከተጠሪ ጋር ካደረጉት የመጀመሪያ የስራ ውላቸው ጋር የተገናኘ ስለመሆኑ አላከራከረም፡፡ ማስረጃዎችን የመስማት፣ የመመርመር እና የመመዘን በህግ ስልጣን የተሰጠው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት አመልካች እና ተጠሪ መስከረም 26 ቀን 2015ዓ.ም ወደፊት በሚከሰት ሁኔታ ላይ የተመሰረተ አዲስ የቅጥር ውል ማድረጋቸውን፣ ውሉ በይዘቱ አመልካች ከመጀመሪያው የስራ ውላቸው ጋር በተገናኘ ምንም የሚያነሱት ጥያቄ የሌለ መሆኑን የሚገልጽ መሆኑን አረጋግጧል፡፡ ሆኖም አመልካች ከመጀመሪያው የስራ ውላቸው ጋር በተገናኘ ምንም የሚያነሱት ጥያቄ የሌለ መሆኑን የተስማሙበት ይህ መስከረም 26 ቀን 2015ዓ.ም የተደረገው የስምምነት ክፍል አመልካች ከመጀመሪያው የስራ ውል ጋር በተያያዘ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ያላቸውን ማንኛውም ጥያቄ በስምምነት ለመፍታት የተደረገ እርቅ ስምምነት ሳይሆን አመልካች ክፍያ የመጠየቅ ህጋዊ መብቱን ለመተው ያደረገው ስምምነት መሆኑን ይህ ችሎት ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ከላይ በተገለጸው የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጁ ድንጋጌ መሰረት ይህ የስምምነት ክፍል የህግ ውጤት አይኖረውም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ጥቅምት 26 ቀን 2011ዓ.ም የተደረገው የስራ ውል የካቲት 2012ዓ.ም ተቋርጧል፤ ከዚህ የስራ ውል ጋር የተያያዙ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የነበሩ ግዴታዎችም መስከረም 26 ቀን 2015ዓ.ም ባደረጉት የስራ ውል ስምምነት መሰረት ቀሪ ያደረጓቸው በመሆኑ አመልካች ተጠሪን የ15,000ዶላር ክፍያ ሊጠይቅ አይገባም በማለት የሰጠውን ብይን እና ይህንኑ ብይን ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት በማጽናት የሰጠውን ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት እና ሊታረም የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የስር የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት መስከረም 26 ቀን 2015ዓ.ም በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተደረገውን ውል ይዘት በመመርመር አመልካች ቦይንግ 777 እና 778 አውሮፕላን ላይ ስልጠና ወስደው ስልጠናውን በብቃት ካጠናቀቁ የስራ ውል ለማቋቋም መሆኑን፤ ነገር ግን ስልጠናውን በብቃት ካልተወጡ የስራ ቅጥር ውሉ ውጤት እንደማይኖረው ወይም ውሉን ያለማስጠንቀቂያ እንደሚያቋርጥ ውሉ የሚገልጽ መሆኑን ያረጋገጠው ጉዳይ ነው፡፡ መስከረም 26 ቀን 2015ዓ.ም በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በዚህ መልኩ በተደረገው ውል መሰረት አዲስ የስራ ውል ለማቋቋም በቅድመ ሁኔታነት የተቀመጠውን ይኀውም አመልካች የተሰጣቸውን ስልጠና በብቃት ለማጠናቀቅ አለመቻላቸውን የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት የአመልካች እና የተጠሪ ምስክሮችን በመስማት አረጋግጧል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የስር የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት አመልካች እና ተጠሪ መስከረም 26 ቀን 2015ዓ.ም ያደረጉት የስራ ውል የተቀመጠለት የአመልካች ስልጠናውን በብቃት ተወጥቶ የማለፍ ሁኔታ ባለመሟላቱ ምክንያት ውጤት ያላገኘ በመሆኑ በዚሁ መነሻ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የስራ ውል ባለመኖሩ የአመልካች ክስ (በመጀመሪያው ውል መሰረት ከሚጠየቅ የክፍያ ጥያቄ ውጪ) የክስ ምክንያት የለውም በማለት የሰጠው ብይን እና ይህንኑ ብይን ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት በማጽናት የሰጠውን ውሳኔ ይህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት በመዝገብ ቁጥር 150714 በ20/10/2015ዓ.ም የሰጠው ብይን እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት በመዝገብ ቁጥር 310394 በ27/3/2016ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሻሽለዋል፡፡
2. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት በመዝገብ ቁጥር 150714 በ20/10/2015ዓ.ም አመልካች እና ተጠሪ መስከረም 26 ቀን 2015ዓ.ም ያደረጉት የስራ ውል የተቀመጠለት የአመልካች ስልጠናውን በብቃት ተወጥቶ የማለፍ ሁኔታ ባለመሟላቱ ምክንያት ውጤት ያላገኘ በመሆኑ በዚሁ መነሻ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የስራ ውል ባለመኖሩ የአመልካች ክስ (በመጀመሪያው ውል መሰረት ከሚጠየቅ የክፍያ ጥያቄ ውጪ) የክስ ምክንያት የለውም በማለት የሰጠው ብይን እና ይህንኑ ብይን ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት በመዝገብ ቁጥር 310394 በ27/3/2016ዓ.ም በማጽናት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ጸንተዋል፡፡
3. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት በመዝገብ ቁጥር 150714 በ20/10/2015ዓ.ም በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ጥቅምት 26 ቀን 2011ዓ.ም ከተደረገው የስራ ውል ጋር የተያያዙ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የነበሩ ግዴታዎችም መስከረም 26 ቀን 2015ዓ.ም ባደረጉት የስራ ውል ስምምነት መሰረት ቀሪ ያደረጓቸው በመሆኑ አመልካች ተጠሪን የ15,000ዶላር ክፍያ ሊጠይቅ አይገባም በማለት የሰጠውን ብይን እና ይህንኑ ብይን ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት በመዝገብ ቁጥር 310394 በ27/3/2016ዓ.ም በማጽናት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽረዋል፡፡
4. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት የዘጋውን የመዝገብ ቁጥር 150714 የሆነውን መዝገብ አንቀሳቅሶ አመልካች ከተጠሪ ጋር ከነበረው የመጀመሪያ የስራ ውል ጋር በተያያዘ ያቀረበውን የክፍያ የዳኝነት ጥያቄ በተመለከተ አመልካች እና ተጠሪን በፍሬጉዳዩ ላይ በማከራከር እና በተገቢዎቹ መንገዶች ሁሉ በማጣራት ጉዳዩን መርምሮ ተገቢ ነው የሚለውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 341(1) መሰረት መልሰንለታል፡፡
5. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍርድቤቶች ይድረስ፡፡
6. መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገ ለግልም!

የሰበር መዝገብ ቁጥር 258091

ህዳር 30 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች፡-----ሽመክት አሰፋ

አለማየሁ ሹናራ

ተናኜ ጥላሁን

ዋዚሞ ዋሲራ

ዘዉዲቱ ታደሰ

አመልካች፡------- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ነ/ፈጅ ጌቱ ዋቅቶላ ቀረቡ

ተጠሪ፡-------- አቶ አገኘሁ ደጉ አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጠ

**ፍርድ**

ለፍርዱ መነሻ የሆነው ጉዳይ የአሰሪ እና ሰራተኛ ክርክርን መሰረት ያደረገ በአ.ብ.ክ.መ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የተጀመረ ክርክር ሲሆን አመልካች ተከሳሽ ሲሆኑ ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ ነበሩ፡፡ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ በአጭሩ፡-በአመልካች ተቋም ውስጥ ከመጋቢት 14 ቀን 2011 ዓ/ም እስከ መጋቢት 18 ቀን 2012 ዓ/ም ድረስ በጊዜያዊነት በከፍተኛ የደንበኞች አገልግሎት ክፍት ቦታ ላይ በደረጃ 11 ተወክዬ ከአንድ አመት በላይ አገልግዬ እያለ በ18ኛው ህብረት ስምምነት አንቀጽ 1.6.5 መሰረት መደቡን በሰው ሀይል ካላስያዘው ተጠሪን በቦታው ላይ የመስጠት ኃላፊነት እያለበት የከለከለኝ በመሆኑ በስራ መደቡ ላይ ከመጋቢት 18 ቀን 2012 ዓ/ም ጀምሮ እንዲመድበኝ እና ቦታው የሚያስገኘውን ደሞዝ እና ጥቅማ ጥቅም ብር 134,014.80/አንድ መቶ ሰላሳ አራት ሺህ አስራ አራት ብር ከሰማንያ ሳንቲም/

እንዲከፈለኝ፣የስራ ልምዱም በደረጃ 11 ከተጠቀሰው ጊዜ ጀምሮ ሊያዝ ይገባል እንዲሁም ወጪ እና ኪሳ ይወሰንልኝ የሚል ነበር፡፡

በተጠሪ የክስ አቤቱታ ላይ አመልካች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማለት ያቀረቡትም ጉዳዩ የህብረት ስምምነት ትርጉምን የሚመለከት ሳይሆን ደረጃ እድገት ይሰጠኝ የሚል በመሆኑ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርዱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም፣ተጠሪ ያቀረበው ክስ ከመጋቢት 17 ቀን 2013 ዓ/ም ጀምሮ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት በአማራጭ መልሳቸው ደግሞ ተጠሪ ለ12.5 ቀናት ፍቃድ ተጠቅሞ ስለነበረ በቦታው ለአንድ አመት አልሰራም፡፡ከመጋበት 12 ቀን 2011 ዓ/ም እስከ ታህሳስ 20 ቀን 2012 ዓ/ም ድረስ በተጠባባቂነት ከሰራ በኂላ የኮምፒዩተር ሲስተሙ ቀድሞ ወደ ነበረበት የደንበኞች አገልግሎት መኮንን ደረጃ 9 መልሶታል፡፡ተጠሪ ሲሰራበት የነበረው ቅርንጫፍ

ከመጋበት 12 ቀን 2011 ዓ/ም እስከ ሰኔ 21 ቀን 2011 ዓ/ም ድረስ ደረጃ አንድ ቅርንጫፍ ስለነበረ ተጠሪ በተጠባባቂነት ሲሰራበት የነበረው ቦታ ደረጃ 10 እንጂ ደረጃ 11 አልነበረም፡፡ቅርንጫፉ ወደ ደረጃ 3 ሲያድግ የስራ መደቦች እድገት ለሰራተኞች ተሰጠ እንጂ ቀጥታ ምደባ ተጠሪ የጠየቁት የደሞዝ ክፍያ በቦታው ላይ ከመጋቢት 18 ቀን 2012 ዓ/ም ጀምሮ እስካሁን ያልሰራበት በመሆኑ ተቀባይነት የለውም እንዲሁም የጠበቃ አበሉም የተጋነነ ነው ሲሉ መልስ ሰጥቷል፡፡

በዚህ መልኩ ግራ ቀኙን ያከራከረዉ የአሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርድ ማስረጃዎችን መዝኖ የተጠሪን ጥያቄ በህብረት ስምምነታችዉ መሰረት ከአንድ አመት በላይ በተጠባባቂነት የሰራሁበትን ቦታ ይሰጠኝ የሚል እንጂ የደረጃ እድገት ይሰጠኝ የሚል ባለመሆኑ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርዱ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ስልጣን አለው፡፡ይርጋን በሚመለከት ተጠሪ በድርጅቱ ውስጥ በውክልና ከተሰጠው ቦታ ላይ ከአንድ አመት ከአራት ቀናት ሰርቶ ቦታው እንዲሰጠው በተደጋጋሚ ጠይቆ አመልካች ይህን አውቆ መልስ ሳይሰጠው ቆይቶ በህዳር 23 ቀን 2014 ዓ/ም ቦታውን እንደማይሰጠው የገለጸ በመሆኑ ይርጋዉ መቆጠር ያለበት በጽሁፍ ተጠሪ ካወቀበት ጀምሮ የይርጋው ጊዜው ያላለፈ በመሆኑ መቃወሚያው ውድቅ ተደረግጓል በማለት በፍሬ ነገር ክርክር ላይ ደግሞ በደረጃ 11 ላይ ተጠሪ በውክልና እስከ መጋቢት 18 ቀን 2012 ዓ/ም ለአንድ አመት ስራውን ስለመስራቱ በግራ ቀኙ ምስክሮች የተረጋገጠ በመሆኑ እንዲሁም ተጠሪ እረፍት መውጣቱ የስራ ዘመኑን የማያቋረጠው በመሆኑ ተጠሪ በውክልና ይዘውት በተመደቡበት ከፍተኛ የደንበኞች አገልግሎት የስራ መደብ ላይ ከመጋበት 18 ቀን 2012 ዓ/ም ጀምሮ እንዲመደቡ እና ለቦታው የተመደበውን ደሞዝ እና ጥቅማ ጥቅም ሊከበር ይገባል ሲል በአብላጫ ድምፅ ፍርድ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በውሳኔው ቅር በመሰኘት ለባህርዳር እና አከባቢዋ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም ግራ ቀኙን አከራክሮ የስር የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ዉሳኔ አፅንቷል፡፡

በመቀጠል አመልካች ለአብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር ቅሬታ ያቀረቡ ቢሆንም መሰረታዊ የህግ ስህተት በስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ አልተፈፀመም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ አፅንቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ለማሳረም በሚል ሲሆን አቤቱታው በአጭሩ ሲታይ፡- ተጠሪ ያቀረቡት ዳኝነት በደረጃ 11 በተጠባባቂነት ለአንድ አመት የሰራሁ በመሆኑ ካለሁበት ደረጃ 9 ወደ 11 ላድግ ይገባል የሚል ስለሆነ የደረጃ እድገትን በሚመለከት ደግሞ ስልጣን ያለው ፍ/ቤት እንጂ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ባለመሆኑ ቦረዱ ያለ

ተጠሪ በተደጋጋሚ አቤቱታ ለአመልካች ማቅረባቸው በአዋጅ ቁጥር 1156/11 አንቀጽ 165 ስር እንደይርጋ ማቋረጫ ባልተቀመጠበት ሁኔታ ይርጋው እንደተቋረጠ ተደርጎ መወሰኑ ሆነ ተጠሪ ከመጋቢት 14 ቀን 2011 እስከ ሰኔ 20 ቀን 2011 ዓ/ም እና ከሰኔ 21 ቀን 2011 እስከ መጋቢት 18 ቀን 2012 ዓ/ም ድረስ በተጠባባቂነት የስራባቸው ሁለት መደቦች እንደ ቅደም ተከተላቸው በደረጃ 10 እና 11 ሲሆኑ ሁለቱም የተለያዩ የስራ መደቦች ሆነው እያለ እንደተመሳሳይ ስራ ተቆጥረው መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲታረም የሚል ነው፡፡

አመልካች ያቀረቡትን የሰበር ቅሬታ መነሻ ተደርጎ በስር ፍ/ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ በውክልና የሰራበት መደብ በህብረት ስምምነቱ መሰረት በደረጃ እድገት እንዲሰጠው የጠየቀው የአሁኑ ተጠሪ ብቻ መሆኑ

ከመረጋገጡ አኳያ የአሰሪ እና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን የስረ ነገር ስልጣን ያለው መሆን አለመሆኑን በአዋጅ ቁጥር 1156/11 አንቀጽ 139፣143፣ እና 148 በኅብረት ስምምነት አንቀጽ 1 አንጻር አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ጉዳዩ በፌደራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 28(3) መሰረት ያስቀርባል ብሏል፡፡

ተጠሪ ባቀረቡት መልስ በስር ፍ/ቤት ያቀረብኩት ክስ የደረጃ እድገት ሳይሆን በህብረት ስምምነቱ መሰረት ከአንድ አመት በላይ ያገለገልኩበት መደብ ላይ በቋሚነት ምደባ ይሰጠኝ የሚል በመሆኑ ይህ ደግሞ የወል የስራ ክርክር በመሆኑ ቦርዱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን አለው፡፡አመልካች ምደባው እንዲሰጠኝ ተጠሪ በተደጋጋሚ የጠየኩ ስለመሆኑ እና አመልካች መደለያ እና ማባባያ ቃል ሲሰጠኝ ቆይቶ መብቴን አውቆ አለመፈጸሙን ከገለጸበት ቀን ጀምሮ ይርጋ ሳያግደው ክስ ያቀረብኩ በመሆኑ የይርጋ ጥያቄው ውድቅ በማድረግ በፍሬ ጉዳዩ ላይ የሰጠዉ ዉሳኔ በአግባቡ ስለሆነ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ይፅናልን ሲሉ መልስ ሰጥቷል፡፡

ይህ ፍርድ ቤትም ያስቀርባል ሲባል የተየዘዉን ጭብጥ መሰረት በማድረግ በስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ሰህተት አለ ወይስ የለም ? የሚለዉን ከሕጉ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ ተመርምሯል፡፡

እኛም መዝገቡን መርምረን እንዳየነዉ አመልካች ባቀረቡት የሰበር ቅሬታ ላይ ተጠሪ የጠየቁት የደረጃ እድገት በመሆኑ ጉዳዩን የማየት ስልጣን ያለዉ መደበኛዉ ፍርድ ቤት እንጂ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ባለመሆኑ ስልጣን በሌለዉ ጉዳይ ላይ የሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢነት የለዉም ሲሉ ተከራክሯል ፡፡ተጠሪ በከፍተኛ የደንበኞች አገልግሎት መደብ በሆነዉ በደረጃ 11 ላይ በዉክልና ከአንድ አመት በላይ የሰራዉ በመሆኑ ቦታዉ በቋሚነት ካልተያዘ በቦታዉ በዉክልና ለሰራዉ ሰራተኛ እንደሚገባዉ በ18 ኛዉ ሕብረት ስምምነት አንቀጽ 1.6.5 ላይ የተገለፀ ስለሆነ ተጠሪ ይህ ቦታ ይገባኛል ብዬ አመልካችን ስጠይቀዉ እንቢተኛ ስለሆነ የተጠቀሰዉ ከፍተኛ የደንበኞች አገልግሎት ደረጃ 11 ላይ እንድመደብ እና ከዚህ ጋር የተያያዘ ያለዉን ጥቅማ ጥቅም ይከፈልኝ ሲል ያቀረቡኩትን የዳኝነት ጥያቄ ላይ ጉዳዩ የወል ክርክር በመሆኑ ጉዳዩን የማየት ስልጣን ያለዉ አካል የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ነዉ በማለት ክርክር አቅርቧል ፡፡

በተየዘዉ ጉዳይ ተጠሪ ለአንድ አመት በዉክልና ለሰራሁበት የስራ መደብ ደረጃ 11 ከፍተኛ የደንበኞች አገልግሎት ላይ በህብረት ስምምነቱ መሰረት እንድመደብ አመልካችን ሲጠይቅ ፈቃደኛ ስላልሆነ በዉክልና በሰራሁበት የስራ መደብ ላይ እንድመደብ እና ለቦታዉ የተያዘዉን ጥቅማ ጥቅም እንዲከፈለኝ ሲሉ

የጠየቁትን ዳኝነት ጥያቄ ላይ በተመለከተ ተጠሪ ባቀረበዉ የመጀመሪያ ደረጃ መቋወሚያ ላይ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለዉም ሲሉ ያቀረቡትን በተመለከተ ተጠሪ ያቀረበዉን የዳኝነት ጥያቄ ላይ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ያለዉ ማነዉ ? የሚለዉን ለመወሰን በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 መሰረት ጉዳዩ የወል ክርክር ወይስ የግል ክርክር የሚለዉ ጉዳይ ምላሽ የሚሻዉ ጉዳይ ሆኖ አግኝተኗል፡፡አንድ የስራ ክርክር የወል ወይም የግል የስራ ክርክር ለማለት መታየት ያለባቸዉን ጉዳዮች በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 16653 እና 18180 ላይ በተሰጠዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም አንድ ክርክር የወል ክርክር ነዉ የሚባለዉን ለመለየት ጉዳዩ የጋራ በሆነ የሰራተኞች መብት እና ጥቅም ላይ አዉንታዊ ወይም አሉታዊ ዉጤት የሚያስከትል ከሆነ ብቻ ክርክሩ እንደ የወል የስራ ክርክር የሚቆጠር ሲሆን የግል የስራ ክርክር ደግሞ ዉጤቱ በአንድ ሰራተኛ ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ጉዳይ ነዉ፡፡

አሁን በእጃችን ባለዉ ጉዳይ ተጠሪ ከፍተኛ የደንበኞች አገልግሎት ደረጃ 11 መደብ ስራ ይሰጠኝ ሲል ያነሳዉ ጥያቄ በ18 ኛዉ የህብረት ስምምነት በተቀመጠዉ መብት አንፃር አንድ ሰራተኛ በአንድ የስራ መደብ ላይ በዉክልና ለአንድ አመት ከሰራ በቦታዉ የተመደመ የሰዉ ኃይል ከሌለ በዉክልና በቦታዉ ለአንድ አመት ለሰራዉ ሰራተኛ የስራ መደቡ እንደሚገባዉ በህብረት ስምምነቱ ላይ በመቀመጡ ምክንያት ሲሆን ይህን መብት ጥያቄ ሊያነሳ የሚገባዉ ተጠሪ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ሰራተኞች እንደ ተጠሪ ያሉት በአንድ የስራ መደብ ላይ ለአንድ ዓመት በዉክልና የሰሩና በቦታዉ የተመደበ የሰዉ ኃይል ከሌለ በዉክልና በሰሩት መደብ ላይ ለመመደብ ጥያቄዉን ለማንሳት በህብረት ስምምነት ላይ የተጠቀሰ መብት በመሆኑ ከዚህ አንፃር ተጠሪ ያነሱት የዳኝነት ጥያቄ በተጠሪ ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሳይሆን ሌላዉም ሰራተኛ በአንድ የስራ መደብ ላይ በዉክልና ለአንድ አመት ከሰራና በቦታዉ የተመደበ የሰዉ ኃይል ከሌለ ይህን በዉክልና በሰራዉ የስራ መደብ ላይ ምደባዉ እና ለመደቡ የተቀመጠዉን ጥቅማ ጥቅም መጠየቅ እንደሚችል ህብረት ስምምነቱ ከመደንገጉ አኳያ ይህ ደግሞ የሚያስገኘዉ መብት እና ጥቅም የሰራተኛዉ የወል መብት እንጂ በአንድ ሰራተኛ ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ደ የግል የስራ ክርክር ያለመሆኑን ስለተገነዘብን የወል የስራ ክርክርን በተመለከተ ጉዳዩን የማየት ስልጣን ያላቸዉ የአሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርድ ስለመሆኑ ከላይ ከተጠቀሰዉ የሰበር ዉሳኔ የተገነዘብን ስለሆነ ከዚህ አኳያ ተጠሪ ያቀረበዉ ክስ የወል የስራ ክርክር በመሆኑ የተጠሪን ዳኝነት ጥያቄ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ አይቶ ዉሳኔ መስጠቱ በአግባቡ ስለሆነ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የሌለ በመሆኑ ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ዉሳኔ**

1/በአ/ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 03-128135 ላይ ታህሳስ 24 ቀን 2016 ዓ፣ም በዋለዉ ችሎት የተሰጠዉ ዉሳኔ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የሌለ በመሆኑ በፌ/ጠ/ፍ/ቤት የሰበር ስነ ስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1)(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2/ ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ወገኖች ይቻቻሉ ፡፡

በዚህ መዝገብ የተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ ካለ ተነስቷል ፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ፋ/ዘ**

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ዉሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 258301

ህዳር 27 ቀን 2017ዓ/ም

ዳኞች፡ ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ብርቅነሽ እሱባለው

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች፡ ፀሐይ ኢንዱስትሪ አ.ማ አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡ 1ኛ. አቶ ጣሂር ሙስጠፋ

2ኛ. አቶ ነብዩ መሀመድ ቀረቡ

3ኛ. አቶ ጌታቸው ባይሳ

4ኛ. አቶ ቃለዓብ ደረጀ

5ኛ. አቶ ወንድወሰን አስናቀ ቀረቡ

6ኛ. አቶ ወርቁ ወየቻ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ የቀረበው አመልካች የፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት በመዝገብ ቁጥር 296546 በ25/4/2016ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት በ20/5/2016ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ስላቀረበ ነው፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

የጉዳዩ አመጣጥ ተጠሪዎች(የስር ከ20ኛ-25ኛ ከሳሾች) በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ( ተጠሪዎች በአመልካች ላይ በስር ፍርድቤት ያቀረቡት ክስ ሌሎች በዚህ የሰበር ክርክሩ ላይ የሌሉ የስር ከ1ኛ እስከ 19ኛ ከሳሾች በሌላ መዝገብ ካቀረቡት ክስ ጋር ተጣምሮ የታየ) በአመልካች ድርጅት በተለያየ የስራ መደብ በቋሚነት እስከ 23/5/2015ዓ.ም እና 23/6/2015ዓ.ም ስናገለግል ቆይተናል፡፡ ሆኖም አመልካች ባስጠናው የደመወዝ ስኬል ጥናት መሰረት የተወሰኑ የስራ መደቦች የሚያስፈልገው የሰው ሀይል ብዛት በመቀነሱ እንዲሁም ሌሎች ደግሞ በመታጠፋቸው በሚል ምክንያት በአዋጁ አንቀጽ 28 መሰረት ከአመልካች ጋር የስራ ውል የተቋረጠ መሆኑን በመግለጽ ከስራ አሰናብቶናል፡፡

ይሁን እንጂ አመልካች ባልከሰረበት እና ትርፋማ ሆኖ ሳለ በአዋጁ አንቀጽ 28 መሰረት የደመወዝ ስኬል መጠናት በሚል ምክንያት ሰራተኛ መቀነስ የሚቻል ስለመሆኑ ፈቃጅ ድንጋጌ በሌለበት ሁኔታ፤ የታጠፈው የስራ መደብ ምን እንደሆነ፤ በምን አግባብ እንደታጠፈ እና ይህም ለሰራተኞቹ በግልጽ ባልተገለጸበት ሁኔታ በአዋጁ ሰራተኛን ለመቀነስ ከሚቻልባቸው ሁኔታዎች ውጪ ምክንያት በመጥቀስ ማሰናበቱ ህገወጥ ነው፡፡ አመልካች የተጠሪዎችን የስራ ውል ካቋረጠ አንድ ወር እንኳ ባልሞላ ግዜ ውስጥ ተጠሪዎች ከዚህ ቀደም በምንሰራበት የስራ መደብ ላይ ግዜያዊ የቅጥር ማስታወቂያ በማውጣት ፈቃደኛ ካለም ከእኛ ውስጥ በግዜያዊነት መቀጠር እንደምንችል በመግለጽ የሰራተኛ ቅጥር ፈጽሟል፡፡ ይህም የሚያሳየው አመልካች ተጠሪዎችን ከስራ ለማሰናበት የገለጻቸው ምክንያቶች ሀሰት እና ሆን ተብሎ ቋሚ ሰራተኛ እንዳይኖር በማሰብ የተደረገ ቅነሳ መሆኑን ነው፡፡

ስለሆነም አመልካች ያደረገው ቅነሳ ህገወጥ እንዲባልና ወደስራ መመለስ የምንፈልገውን ተጠሪዎች በስራችን ላይ ብንቆይ ልናገኝ ከምንችለው ጥቅማጥቅም ጋር ታስቦ ወደስራችን እንድንመለስ እንዲወሰንልን፤ ወደስራ መመለስ ለማንፈልገው ተጠሪዎች ደግሞ የካሳ ክፍያና ጉዳዩ ውሳኔ እስኪያገኝ ልናገኝ ይገባ የነበረውና ያልተከፈለን ደመወዝ ታስቦ አመልካች እንዲከፍለን እንዲወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎችንም አቅርበዋል፡፡

አመልካች ባቀረበው መልስ የተጠሪዎች የስራ ውል የተቋረጠው በህግ አግባብ የተጠናን አዲስ የመዋቅር ጥናት ተከትሎ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 28(3)(ሐ) በሚፈቅደው መሰረት አመልካች የድርጅቱን ምርታማነት ለማሳደግ በባለሙያ አዲስ አደረጃጀት አስጠንቶ ተግባራዊ ሲያደርግ የአሰራር ዘዴዎች በመለወጣቸውና ከዚህ ጋር ተያይዞ ሰራተኛ መቀነስ በማስፈለጉ ነው፡፡ ይኸውም አመልካች ጥሬ እቃ ከውጪ እያስመጣ የሚያመርት ድርጅት በመሆኑና አሁን ባለው ሁኔታ ከፍተኛ የሆነ የጥሬ እቃ እጥረት በመኖሩ በዚህ ሁኔታ ምርታማና አትራፊ ሆኖ ለመቀጠል ምን አይነት የአሰራር ዘዴን መከተል እንዳለበት ምክር ስራ ኃ/የተ/የግ/ማህበር በተባለ የመዋቅር አጥኚ ድርጅት አማካኝነት ሊከተለው የሚገባን የአሰራር ዘዴ አስመልክቶ ጥናት አሰርቷል፡፡ በዚሁ መሰረት በ15/2/2015ዓ.ም የቀረበው የባለሙያ የጥናት ውጤትም ድርጅቱ ትርፋማ ሆኖ እንዲቀጥል በተወሰኑ የስራ መደቦች ላይ የሰራተኛ ቁጥር መቀነስ

እንዳለበት እና የምርት የስራ መደቦች ደግሞ ጥሬ እቃ ሲገኝ ብቻ የሚሰራባቸው በመሆኑ ከቋሚ የስራ መደብ ወደ ኮንትራት የስራ መደብ መቀየር እንዳለባቸው አሳይቷል፡፡ በዚህ መነሻ በምርት ረዳት የስራ መደብ ቋሚ ሰራተኞች የነበሩትን ህጉ በሚፈቅደው አግባብ የማስጠንቀቂያ ግዜ በመስጠት የስራ ውል ተቋርጧል፡፡ ሌሎች ከሳሾች ደግሞ በኦፕሬተር ቴክኒሺያን፣ በቀለም ቅብና በበያጅነት የስራ መደብ ላይ ተመድበው ይሰሩ የነበረ ሲሆን ጥናቱ በነዚህ የስራ መደቦች ላይ ያለው የሰራተኛ ቁጥር መቀነስ እንዳለበት በማረጋገጡ በስራ መደቡ ላይ ከነበሩት ሌሎች ሰራተኞች ጋር ተወዳድረው ባገኙት ውጤት መሰረት ምደባ ሊያገኙ ስላልቻሉ የተቀነሱ ናቸው፡፡ አመልካች ከላይ በተገለጸው ሁኔታ የተጠሪዎችን የስራ ውል ያቋረጠው በህግ አግባብ በመሆኑ ወደ ስራ ሊመልስም ሆነ ካሳ እና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን ሊከፍል አይገባም፡፡ ስለሆነም ክሱ ውድቅ እንዲደረግ በማለት ተከራክሯል፡፡ ማስረጃዎችንም አቅርቧል፡፡

ፍርድቤቱም ክሱን ሰምቶ የአመልካች እና የተጠሪዎችን ምስክሮች ከሰማ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ባጋጠመው የውጪ ምንዛሪ እጥረት ምክንያት ባጋጠመው የጥሬ እቃ እጥረት መነሻነት ኪሳራ ላይ ከመውደቁና ሰራተኛን ከመበተኑ አስቀድሞ ጥናት በማስጠናት በቋሚነት ይሰራበት የነበረውን የስራ መደብ ጥሬ እቃው ሲገኝ ብቻ ተቀጥረው የሚሰሩ ግዜያዊ ሰራተኞችን ቀጥሮ ለማሰራትና በሶስት ፈረቃ ይሰራ የነበረውን ስራ በአንድ ፈረቃ እንዲሰራ ሲደረግ በሶስት ፈረቃ ሲሰራ በነበረበት ግዜ የሚያስፈልገውን የሰው ሀይል ይዞ መቀጠል ስለማይችል የሰራተኞችን ቁጥር አፈጻጸማቸውን መነሻ አድርጎ ቅነሳ ማድረጉ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 28(3)(ሐ) ድንጋጌ የተፈቀደለትን የአሰራር ዘዴውን የመለወጥ ስልጣኑን መጠቀሙን የሚያሳይ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች ለተጠሪዎች የሚገባቸውን ክፍያዎች ከፍሎ የስራ ውላቸውን ማቋረጡ በህጉ አግባብ ነው፤አመልካች ለተጠሪዎች ውዝፍ ደመወዝ ከፍሎ ወደ ስራ ሊመልስም ሆነ ካሳ ሊከፍል አይገባም በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪዎች ከላይ በተገለጸው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት አቅርበው ፍርድቤቱም የአመልካችን መልስ ተቀብሎ ጉዳዩን መርምሮ አንድ አሰሪ ድርጅት ሰራተኞችን ሊቀንስ የሚችለው የድርጅቱን ምርታማነት ለማሳደግ፣ የአሰራር ዘዴዎችን ለመለወጥ ወይም በአዲስ ቴክኖሎጂ ለመጠቀም ሲፈልግ ነው እንጂ የጥሬ እቃ እና የውጭ ምንዛሪ እጥረት ሲያጋጥመው አይደለም፡፡ ይህ ሆኖ አመልካች ስራውን እንዳስቀጠለው መዝገቡ ያስረዳል፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድቤት የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 28(3)(ሐ)ን ለአግባብ በመተርጎም የተጠሪዎች ስንብት አግባብ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ነው በማለት ውሳኔውን በመሻር አመልካች ተጠሪዎችን ማሰናበቱ ህገወጥ ነው፣ ስለሆነም ተጠሪዎችን ወደነበሩበት ስራ አመልካች እንዲመልሳቸው በማለት ወስኗል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ከላይ የተገለጸውን የፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤትን ውሳኔ በመቃወም ሲሆን ይዘቱም ከውጭ ምንዛሪ እጦት ጋር ተያይዞ የተፈጠረው የጥሬ እቃ እጥረት ለተደረገው የአሰራር ዘዴ ለውጥ መነሻዎች እንጂ በራሳቸው ለሰራተኞች ቅነሳ ምክንያቶች አይደሉም፡፡ ይኸውም አመልካች

ለምርቱ የሚሆነውን ጥሬ እቃ ሙሉ በሙሉ ከውጪ የሚያስመጣ ሲሆን አሁን ባለው የውጭ ምንዛሬ እጥረት ምክንያት ጥሬ እቃ በበቂ መጠን ማስመጣት ባለመቻሉ በዚህ አዲስ ሁኔታ ምክንያት ድርጅቱ ቀድሞ ይሰራበት የነበረን አሰራር ዘዴ ይዞ ሊቀጥል አልቻለም፡፡ በመሆኑም ለችግሩ መፍትሄ ለማግኘት የባለሙያ ጥናት አስጠንቶ ጥናቱም ድርጅቱ አዲስ የአሰራር ዘዴን መከተል እንዳለበት ይኀውም የችግሩ መነሻ ጥሬ እቃ በመሆኑ ጥሬ እቃ ያለምንም ችግር ይኖራል በሚል ተዘጋጅቶ የነበረው ቋሚ የምርት ደራት የስራ መደብ እንዲታጠፍ(እንዲሰረዝ) እና ጥሬ እቃ ሲገኝ ብቻ እየተቀጠሩ ጥሬ እቃው ሲያልቅ በሚሰናበቱ ግዜያዊ ሰራተኞች እንዲሰራ እንዲሁም ቀደም ሲል የነበረው የሶስት የስራ ሺፍት ወደ አንድ ሺፍት እንዲመጣ የሚያዝ ነው፡፡ ተጠሪዎች ይህ አዲስ የአሰራር ዘዴ ሲተገበር የስራ ውላቸው የተቋረጠባቸው ናቸው፡፡ ይህ አዲስ የአሰራር ዘዴ የተተገበረው የሰራተኛ ማህበሩ መሪዎች የኮሚቴ አባላት ሆነው በተሰራ ስራ ሲሆን ተጠሪዎችም ይህን ተቀብለው ከዚህ ጋር ተያይዘው የሚከፈሉ ክፍያዎችን በሙሉ ወስደዋል፡፡ በዚሁ አግባብ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 28(3)(ሐ) ከደነገገው አንጻር አመልካች ተጠሪዎችን ከስራ ማሰናበቱ አግባብ ሆኖ ሳለ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት አመልካች ተጠሪዎችን የጥሬ እቃ እና የውጭ ምንዛሪ እጥረት አጋጥሞኛል በሚል ምክንያት ማሰናበቱ አግባብ አይደለም በማለት ፍሬነገርን በተሳሳተ ሁኔታ በመውሰድ እንዲሁም የተሻለ ምክንያት ሳያቀርብ የስር ፍርድቤትን ውሳኔ በመሻር የተጠሪዎች ስንብት ህገወጥ ነው፤ ተጠሪዎች ወደ ስራ እንዲመለሱ በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲሻር እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት ውሳኔ እንዲጸና የሚል ነው፡፡

የሰበር አቤቱታው በሰበር ችሎቱ ተመርምሮ አመልካች በውጭ ምንዛሬ ምክንያት ለኢንዱስትሪ ስራ ጥሬ እቃ እጥረት ገጥሞኛል በሚል በባለሙያ አስጠንቶ ተጠሪዎችን የቀነሰው በህግ አግባብ መሆን አለመሆኑን ከአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 28(3) እና ሌሎች አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንጻር ለማጣራት ያስቀርባል በማለት በ30/7/2016ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ መሰረት ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጓል፡፡ ተጠሪዎችንም በ15/9/2016ዓ.ም በተጻፈ ባቀረቡት መልስ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት የሰጠው ውሳኔ አግባብ ነው የሚሉበትን ምክንያት በመዘርዘር እንዲጸና ጠይቀዋል፡፡ አመልካች በ3/10/2016ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታውን አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢዎቹ የህግ ድንጋጌዎች አንጻር የስር የፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸውን የመጨረሻ ውሳኔዎች ማረም ስለመሆኑ በኢፌዲሪ ህገመንግስት አንቀጽ 80(3)(ለ) እንዲሁም በፌደራል ፍርድቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4) እና 10(1) በተዘረዘሩት ድንጋጌዎች ተቀምጧል፡፡ አንድ

ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻለው በፌደራል ፍርድቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4) ከ "ሀ-ሸ " ከተዘረዘሩት ውስጥ ቢያንስ አንዱን የሚያሟላ ሆኖ በውጤቱም ፍትሕን የሚያዛባ ጉልህ የህግ ስህተት የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 2(4) ድንጋጌ ይዘት የሚያስገነዝብ ነው።

የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 28(3)(ሐ) የድርጅቱን ምርታማነት ለማሳደግ፣ የአሰራር ዘዴዎችን ለመለወጥ ወይም በአዲስ ቴክኖሎጂ ለመቀጠል ሲባል የሚደረግ የስራ ውል ማቋረጥ የሚያስከትል ውሳኔ የስራ ውልን በማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ በቂ ይሆናል በማለት ደንግጓል። የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 182(1) የይግባኝ ሰሚ ፍርድቤት በሚሰጠው የፍርድ ውሳኔ የመጀመሪያውን ደረጃ ፍርድቤት ፍርድ ያሻሻለው ወይም የለወጠው እንደሆነ በትችቱ ላይ ለይግባኝ ባዩ የሚገባውን ዳኝነት በዝርዝር መግለጽ አለበት በማለት ደንግጓል። የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 38844(ቅጽ 8) ይግባኝ ሰሚው ፍርድቤት በስር ፍርድቤት የተሰጠውን ውሳኔ ሊሽር የሚችለው በስር ፍርድቤት የተሰጠውን ምክንያትና ማብራሪያ የማይቀበልበትን ምክንያት በመግለጽ፣ ማስረጃዎችን በመመዘን እና ከህጉ ጋር ያላቸውን ተዛማችነት በማብራራት እንጂ የስር ፍርድቤት የሰጠውን ውሳኔ በአግባቡ ሳይመረምር እና ለውሳኔው በቂ ምክንያት ሳይሰጥ መሻር የማይችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 182(1) ድንጋጌን በማጣቀስ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል።

በያዝነው ጉዳይ ፍሬነገርን በማስረጃ የማጣራት በህግ ስልጣን የተሰጠው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት የአመልካች እና የተጠሪዎችን ምስክሮች በመስማት ከቀረቡት የሰነድ ማስረጃዎች ጋር መርምሮ አመልካች ባለበት የጥሬ እቃ እጥረት ምክንያት ምርታማ እና አትራፊ ሆኖ ለመቀጠል ምን አይነት የአሰራር ዘዴን መከተል እንዳለበት በመዋቅር አጥኚ ድርጅት ማስጠናቱን፣ ጥናቱም ድርጅቱ ትርፋማ ሆኖ እንዲቀጥል በተወሰኑ የስራ መደቦች ላይ የሰራተኛ ቁጥር መቀነስ እንዳለበትና የምርት ረዳት የስራ መደቦች ደግሞ ጥሬ እቃ ሲገኝ ብቻ የሚሰራባቸው በመሆኑ ከቋሚ የስራ መደብ ወደ ኮንትራት የስራ መደብ መቀየር እንዳለባቸው ማሳየቱን ያረጋገጠው ፍሬጉዳይ ነው። ይህ ከሆነ ደግሞ ፍርድቤቱ አመልካች ጥናት በማስጠናት በቋሚነት ይሰራበት የነበረውን የስራ መደብ ጥሬ እቃው ሲገኝ ብቻ ተቀጥረው የሚሰሩ ግዜያዊ ሰራተኞችን ቀጥሮ ለማሰራትና በሶስት ፈረቃ ይሰራ የነበረውን ስራ በአንድ ፈረቃ እንዲሰራ ሲደረግ በሶስት ፈረቃ ሲሰራ በነበረበት ግዜ የሚያስፈልገውን የሰው ሀይል ይዞ መቀጠል ስለማይችል የሰራተኞችን ቁጥር አፈጻጸማቸውን መነሻ አድርጎ ቅነሳ ማድረጉ አግባብ ነው በማለት ከዚህ አንጻርም አመልካች ለተጠሪዎች የሚገባቸውን ክፍያዎች ከፍሎ የስራ ውላቸውን ማቋረጡ በህጉ አግባብ ነው፣ አመልካች ለተጠሪዎች ውዝፍ ደመወዝ ከፍሎ ወደ ስራ ሊመልስም ሆነ ካሳ ሊከፍል አይገባም በማለት የሰጠው ውሳኔ ከአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 28(3)(ሐ) ድንጋጌ አንጻር አግባብነት ያለው ውሳኔ ነው። ይህ ሆኖ ሳለ ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት አመልካች ተጠሪዎችን ያሰናበተው የጥሬ

እቃ እና የውጭ ምንዛሬ እጥረት ስላጋጠመኝ ነው በሚል እንደሆነ በመውሰድ አንድ አሰሪ ድርጅት ሰራተኞችን ሊቀንስ የሚችለው የድርጅቱን ምርታማነት ለማሳደግ፤ የአሰራር ዘዴዎችን ለመለወጥ ወይም አዲስ ቴክኖሎጂ ለመጠቀም ሲፈልግ እንጂ የጥሬ እቃ እና የውጭ ምንዛሬ እጥረት ሲያጋጥመው አይደለም በማለት በፍሬነገር ደረጃ በስር ፍርድቤት ከላይ በተገለጸው መልኩ ተረጋግጦ የተሰጠ ውሳኔን ያለ ህጋዊ እና በቂ ምክንያት በመሻር አመልካች ተጠሪዎችን ከስራ ማሰናበቱ ህገወጥ ስለሆነ ወደ ነበሩበት ስራ እንዲመልሳቸው በማለት የሰጠው ውሳኔ ሊታረም የሚገባው መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ይህ ችሎት አግኝቶታል፡፡ ስለሆነም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት በመዝገብ ቁጥር 296546 በ25/4/2016ዓ.ም የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት በመ.ቁ 108414 በ8/10/2015ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ በመሻር አመልካች ተጠሪዎችን ከስራ ያሰናበተበት አግባብ ህገወጥ ስለሆነ ወደነበሩበት ስራ እንዲመልሳቸው በማለት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት በመ.ቁ 108414 በ8/10/2015ዓ.ም አመልካች የተጠሪዎችን የስራ ውል ያቋረጠው በህግ አግባብ ነው፤ አመልካች ለተጠሪዎች ውዝፍ ደመወዝ ከፍሎ ወደ ስራ ሊመልስም ሆነ ካሳ ሊከፍል አይገባም በማለት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
3. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍርድቤቶች ይድረሳቸው፡፡
4. መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መ/ቁጥር 258626

ህዳር 26 ቀን 2017 ዓ/ም

ዳኞች - ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

ብርቅነሽ እሱባለዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች ፡- አቶ ጌታቸዉ በላይነህ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- ሰበታ አግሮ ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ተወካይ ደረሰ ረጋሳ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከለታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የስራ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረዉ በሰበታ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካች የወረዳው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 30033 ጥቅምት 28 ቀን 2016 የሰጠዉን ዉሳኔ፣ ይግባኝ ሰሚው የሸገር ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 48169 ህዳር 14 ቀን 2016 ዓ/ም የሰጠዉን ትዕዛዝ እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 437513 ጥር 07 ቀን 2016 ዓ/ም ያሳለፈዉን ዉሳኔ በመቃወም ነው፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው አመልካች ባቀረቡት ክስ በተጠሪ ድርጅት ዉስጥ የጥገና ስራ ኃላፊ ሆኜ በወር ብር 20,250.00 (ሃያ ሺ ሁለት መቶ ሃምሳ) ደመወዝ ተቀጥሬ በመስራት ላይ እያለሁ የተለያዩ ዘዴዎችን በመፍጠር ጠቅላላ አገልግሎት ክፍል እና የጥገና ክፍል በአንድ እንዲደራጅ የተደረገና አንድ ኃላፊ ተመድቦበታል በማለት ከሚያዝያ 30 ቀን 2015 ዓ/ም ጀምሮ የስራ ዉሉ ተቋርጧል በማለት የአንድ ወር ማስጠንቀቂያ በመስጠት ስራ እንዳቆም አሳውቆኛል፡፡ ሁለቱ የስራ ክፍሎች እንደ ሙያ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

መዋህድ የማይቻልና በአንድ ቦታም ሳይቀላቀሉ ከህግ ዉጭ የስራ ዉሉን ያቋረጠ በመሆኑ ስንብቱ ህገወጥ ነዉ ተብሎ ለህገወጥ ስንብት የተቀመጠ ክፍያ ብር 227,475.00 (ሁለት መቶ ሃያ ሰባት ሺ አራ መቶ ስባ አምስት) እንዲከፈለኝ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡

ተጠሪ በሰጠው መልስ ድርጅቱ ምርታማነትን ለመጨመር ሲባል ኤልኤም ግሩፕ በተባለ ድርጅት በ2015 ዓ/ም ባደረገዉ ጥናት መሰረት አመልካች የሚሰራበት የጥገና ክፍል እና ጠቅላላ ክፍል በአንድ ቦታ ተጠቃለው ጠቅላላ አገልግሎት እና ጥገና ክፍል ተብሎ ተደራጅቶ በአንድ አመራር ስር እንዲተዳደር ተጠንቶ ያለቀ በመሆኑ ድርጅቱ ለአመልካች በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀፅ 28 መሰረት የአንድ ወር የፁሁፍ ማስጠንቀቅያ በመስጠት የስራ ዉሉን በህግ አግባብ ያቋረጠ እና አመልካችም በማስጠንቀቅያ በነበሩበት ወቅት ደመወዛቸዉ፣ የአመት እረፊት ክፍያ እና የሰኔ ወር 7 ቀን ደመወዝ በሂሳብ ቁጥራቸዉ ገቢ የተደረገ በመሆኑ ስንበቱ ህጋዊ ነዉ ተብሎ ክሱ ዉድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የወረዳው ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክስ እና ማስረጃ ሰምቶ የድርጅቱን ምርታማነት ለመጨመር ሁለቱ ክፍሎች በአንድ ተቀላቅለዉ በአንድ አመራር እንዲተዳደሩ የተደረገ መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ በአስሪና ሰራተኛ አዋጂ ቁጥር 1156/2011 አንቀፅ 28(3)(ሐ) እና 29(3) መሰረት ስንበቱ ህጋዊ ነዉ፤ ተጠሪ አመልካች ማስጠንቀቅያ ላይ በነበረበት ወቅት ደመወዝና የአመት እረፍት ወደ ገንዘብ ቀይሮ ወደ አመልካች የሂሳብ ቁጥር ያስገባ በመሆኑ የአመልካች ክስ ዉድቅ ሆኗል በማለት ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝተዉ ለሸገር ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ይግባኝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረት ተሰርዟል፡፡ በመጨረሻም የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አቅርበዋል፡፡ ችሎቱ ቅሬታውን መርምሮ ያስቀርባል ብሎ ካከራከረ በኃላ ውሳኔውን አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው ለዚህ ፍርድ ቤት የቀረበው በዚህ ነው፡፡ አመልካች ጥር 23 ቀን 2016 ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተፈፀመ የሚሉትን ስህተት በመዘርዘር በድርጅቱ ተደረገ በተባለዉ የመዋቅር ማሻሻያ የጥገና ክፍል ተሰርዞ ወደ ጠቅላላ አገልግሎት ክፍል የገባ እና በአንድ ላይ በአንድ ሃላፊ መመራቱ በዚህ ክፍል ዉስጥ የያዝኩትን የስራ መደብ የማያሳጣኝ እና የስራ መደቡ ባልተሰረዘበት እንዲሁም በድርጅቱ ዉስጥ ተዘዋዉሬ ልሰራ የምችልብት የስራ መደብ እያለ የስር ፍርድ ቤት አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀፅ 28(3ሐ) አንድ ሰራተኛ በማስጠንቀቅያ የሚሰናበተዉ ሰራተኛዉ የያዘዉ የስራ መደብ የተሰዘረ እና በሌላ የሰራ መደብ መዘወር የማይችል ሆኖ ሲገኝ ብቻ ሆኖ ሳለ ይህን ድንጋጌ በመጥቀስ ስንብቱ ህጋዊ ነዉ ማለቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊተራም ይገባል፡፡ ስንብቱ ህጋዊ ነዉ አይደለም፤ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀፅ 28(3ሐ) መሰረት መደረጉ የህግ ድጋፍ አለዉ የለዉም የሚለዉ ከሚመለከተዉ አካል ማስረጃ ቀርቦ ሳይረጋገጥ እና የተጠየቁት ክፍያዎችን ተጠሪ መክፈሉ

ሳይረጋገጥ በደፈናዉ ስንብቱ ህጋዊ ነዉ ተብርሎ ክሱ ዉድቅ መደረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ይሻርልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ቅሬታው ተመርምሮ የስራ መደብ ለማዋሃድ ተጠሪዉ ባደረገዉ ጥናት አመልካች ሲሰሩበት የነበረዉ የስራ መደብ በሌላ መደብ ስር ገብቷል በሚል ተጠሪ ክርክር በማቅረቡ ብቻ አመልካችን ከስራ ማሰናበቱ ህጋዊ ነዉ ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች የተላለፈዉ ዉሳኔ ተረጋገጠ የተባለዉን ፍሬ ነገር እና የአስሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀፅ 28(1)(መ) ይዘትና ትክክለኛ አፈፃፀም መሰረት ያደረገ መሆን አለመሆኑን አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ጉዳዩ ያስቀርባል ተብሎ መልስ እንዲያቀርብ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ ሰኔ 27 ቀን 2016 ዓ/ም በተፃፈ መልስ አመልካች ይሰሩበት የነበረዉ የተሽከርካሪ እና ጥገና የስራ ክፍል ዉስጥ ሲሆን የጠቅላላ አገልግሎት እና የተሽከርካሪ ጥገና ስራ ክፍል  ሁለቱ ተመሳሳይ የስራ ክፍሎች ወደ አንድ የስራ ክፍል ሲዋቀሩ ለአመልካች ቦታ በመታጣቱ ምክንያት በአስሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀፅ 28(3ሐ)  መሰረት በህግ አግባብ የተሰናበቱ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ መሰረታዊ ስህተት የለበትም፡፡ አመልካች ይሰሩበት የነበረው  የመኪና ጥገና አገልግሎት ክፍል የድርጅቱን ምርታማነት ለመጨመር በተደረገዉ የመዋቅር ጥናት በበቂ ምክንያት መደቡ የተሰረዘ በመሆኑ ተጠሪ የተሰናበተዉ በህግ አግባብ እና የሚገባዉ ክፍያ የተከፈለዉ መሆኑን ክፍያዉ ገቢ የተደረገ ለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት በአግባቡ አጣርቶ ስንበቱ ህጋዊ ነዉ በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ ስህተት የሌለበት በመሆኑ ዉሳኔው ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት ባጭሩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራቀኙን ክርክር በዚህ ሰበር ችሎት ከተያዘው ጭብጥ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለወ መርምሯል፡፡ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደሚቻለዉ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ለጠየቁት ዳኝነት መሰረት ያደረጉት አመልካች የስራ ዉሉን ከህግ አግባብ ዉጪ ማቋረጡን ሲሆን፣ አመልካች በበኩሉ የስራ ዉሉ መቋረጡን ሳይክድ ስንብቱ ህጋዊ ነዉ በማለት የሚከራከረዉ የስራ ዉሉ የተቋረጠዉ ድርጅቱ ባደረገዉ ጥናት አመልካች የሚሰሩበት የጥገና ክፍል እና ጠቅላላ ክፍል በአንድ ቦታ ተጠቃለው ጠቅላላ አገልግሎት እና ጥገና ክፍል ተብሎ ተደራጅቶ በአንድ አመራር ስር እንዲተዳደር በመደረጉ ምክንያት መሆኑንና ሁለቱ የስራ ክፍሎች ወደ አንድ የስራ ክፍል ሲዋቀሩ ለአመልካች ቦታ በመታጣቱ ምክንያት ስንብት መደረጉንም በመጥቀስ ነው፡፡

እንደሚታወቀው የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 የስራ ዉል በህግ፣ በስምምነት እንዲሁም በአሠሪዉ ወይም በሠራተኛዉ አነሳሽነት ሊቋረጥ የሚችልባቸዉን ሁኔታዎች በዝርዝር ይደነግጋል፡፡ የስራ ዉል በህግ የሚቋረጥበት ሁኔታ በአዋጁ አንቀጽ 24 ላይ የተመለከተ ሲሆን፤ በአሠሪዉ አነሳሽነት የሚቋረጠዉ ደግሞ በአንቀጽ 27፣ 28 እና 29 ላይ በተመለከቱት ሁኔታዎች ነዉ፡፡ ስለሆነም አሠሪዉ በተለይም በእራሱ አነሳሽነት የስራ ዉሉን ከማቋረጡ ወይም የስንብት እርምጃ ከመዉሰዱ በፊት

ሠራተኛዉን ከስራ ለማሰናበት የሚያስችል ህጋዊ ምክንያት መኖር አለመኖሩን በአዋጁ ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች አንፃር በጥንቃቄ እንዲመለከት ይጠበቃል፡፡

በተያው ጉዳይ ተጠሪ ለስንብቱ ከጠቀሰው ምክንያት አንፃር የማሰናበት እርምጃው ህጋዊ መሆን አለመሆኑ የሚመረመረዉ በማስጠንቀቂያ የስራ ዉልን ማቋረጥ የሚቻልበትን ሁኔታ አስመልክቶ በአዋጁ አንቀጽ 28 ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች አንፃር ነዉ፡፡ በዚህ አንቀጽ ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ዉስጥ ከአመልካች ክርክር መሠረታዊ ይዘት አኳያ አግባብነት ያለዉ ድንጋጌ በአንቀጽ 28(1)(መ) ስር የተመለከተዉ ነዉ፡፡ ይህ ንዑስ ድንጋጌ እንደሚያሳየው ሠራተኛዉ የያዘዉ የስራ መደብ በበቂ ምክንያት ሲሰረዝና ሠራተኛዉን ወደ ሌላ ስራ ማዛወር የማይቻል ሆኖ ሲገኝ አሠሪዉ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ የስራ ዉሉን መሰረዝ እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም በዚህ መልኩ ሠራተኛዉን ወደ ሌላ ስራ ማዛወር የማይቻል መሆን አለመሆኑ በአግባቡ ሳይጣራ የሚሰጥ ውሳኔ ህጉን የተከተለ አይሆንም፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ አመልካች ስንብቱ ህጋዊ የሚባለው ሰራተኛዉ የያዘዉ የስራ መደብ በአግባቡ የተሰረዘ እና በሌላ የሰራ መደብ መዛወር የማይችል ሆኖ ሲገኝ ብቻ መሆኑን ጠቅሰው የሚከራከሩ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ ሁለቱ የስራ ክፍሎች ወደ አንድ የስራ ክፍል በጥናት በአግባቡ መዋቀራቸወን እና ለአመልካች ቦታ በመታጣቱ ምክንያት ስንብት መደረጉን ተከራክሯል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ እንዳቀረበው ክርክር ለአመልካች ቦታ መታጣቱ በፍሬ ነገር ደረጃ ሳይጣራ በስር ፍርድ ቤቶች ስንብቱ ህጋዊ ነው ተብሎ መወሰኑ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጁን 1156/2011 አንቀጽ 28(1/መ/ መሠረት ያላደረገ በመሆኑ ውሳኔው የሚነቀፍ ነው፡፡

በአጠቃላይ የአመልካችን ክርክር ዉድቅ በማድረግ የስር ፍርድ ቤቶች ያሳለፉት ውሳኔና ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የሰበታ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 30033 ጥቅምት 28 ቀን 2016 የሰጠዉ ዉሳኔ፣ ይግባኝ ሰሚው የሸገር ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 48169 ህዳር 14 ቀን 2016 ዓ/ም የሰጠዉ ትዕዛዝ እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 437513 ጥር 07 ቀን 2016 ዓ/ም ያሳለፈዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የሰበታ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ 1156/2011 አንቀጽ 28(1)(መ) መሠረት አመልካችን ወደሌላ የሰራ መደብ መዛወር የማይቻል መሆን አለመሆኑን በአግባቡ በማጣራት የሚያስከትለውን ህጋዊ ውጤት በተመለከተ በዝርዝር

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

በምክንያት የተደገፈ ውሳኔ እንዲሰጥ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 343(1) መሰረት ጉዳዩን መልሰናል፡፡ የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይድረሰው፡፡

3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

ውሳኔው ታህሳስ 9/2017 ዓ.ም ተነቧል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**የልዩነት ሃሳብ**

ስሜ በተራ ቁጥር አምስት ላይ የተሰየምኩት ዳኛ ከአብላጫው ሃሳብ የተለየሁበትን ምክንያት እንደሚከተለው አስፍሬያለሁ፡፡

በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 መሰረት የስራ ውል የሚቋጠው አንደኛ በህግ ወይም በስምምነት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በተዋዋይ ወገኖች አነሳሽነት ነው፡፡ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011አንቀጽ 24 በህግ መሰረት ውል የሚቋረጥባቸው ምክንያቶች ተዘርዝረዋል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 25 ደግሞ በስምምነት ውል ስለሚቋረጥበት ሁኔታ ይገልጻል፡፡ በአሰሪው አነሳሽነት የስራ ውል የሚቋረጥበት ሁኔታ በአዋጁ ከአንቀጽ 26-30 በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 31 እና 32 ደግሞ በሰራተኛው አነሳሽነት የስራ ውል የሚቋረጥበትን ሁኔታ ደንግጓል፡፡ ከእነዚህ ማዕቀፎች ውጭ አሰሪው ሰራተኛን ከስራ ሲያሰናብት ህገ ወጥ የስራ ስንብት ይሆናል፡፡

አመልካች ከህግ ውጭ የስራ ውሌ ተቋርጧል በማለት ክስ ያቀረቡ ሲሆን ተጠሪ ደግሞ የሚከራከረው ድርጅቱ አዲስ አወቃቀር ሲሰራ አመልካች ሲሰሩበት የነበረው የስራ መደብ በመሰረዙ ምክንያት ስለሆነ ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች ድርጅቱ ጥናት አድርጎ በተሰራ መዋቅር ምክንያት የአመልካች ሲሰሩበት የነበረው የስራ መደብ መሰረዙ ላይ የፍሬ ነገር ድምድሜ ላይ ደርሷል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በኢፌዲሪ ህገ መንግስቱ አንቀጽ 80(3) ሆነ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2/4/ እና 10/1/ መሰረት ውሳኔው ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተትን ማረም እንጂ የፍሬ ነገር ክርክርን የመመርመር ስልጣን የለውም በዚህ ምክንያት የፍሬ ነገር ድምዳሜ ተቀባይነት ያለው ነው፡፡

በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 28/1/መ መሰረት የስራ መደብ በበቂ ምክንያት ሲሰረዝ የሚለውና በአንቀጽ 28(3) (ሐ) አዲስ የአሰራር ዘዴ ሲለወጥ /አዲስ አደረጃጀት/ የሚኖረው የስራ መደብ ለውጥ ሁለቱ ድንጋጌዎች አወንታዊ ውጤት በሚሰጡበት አግባብ መተርጎም ይኖርበታል፡፡ ተጠሪ የአዲስ አወቃቀር በመስራቱ ምክንያት አመልካች የሚሰሩበት የስራ መደብ መታጠፉ በህጉ የስራ ውል በህግ አግባብ የሚቋረጥበት መንገድ አንዱ ሲሆን በአንቀጽ 28(3)(ሐ) እንደተመለከተው የአሰራር ዘዴ ለውጡ ውጤት በመሆኑ ሰራተኛውን ወደ ሌላ የስራ መደብ የማዛወር ግዴታ በህጉ ላይ አሰሪው ላይ አልተጣለበትም በህጉ አንቀጽ 28(1/መ) የተመለከተው ከአሰራር ዘዴ/መዋቅር/ ለውጥ ውጭ የስራ መደብ በበቂ ምክንያት በሚታጠበትን ሁኔታ የሚያስቀመጥ ነው፡፡ በህጉ አሰሪው ላይ ያልተጣለውን ግዴታ መሰረት በማድረግ መወሰኑ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች የስራ ውሉ መቋረጡ በህግ አግባብ የተደረገ ስንብት በመሆኑ ውሳኔው ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም በማለት በሃሳብ ተለይቻለሁ፡፡

ፋ/ዘ

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መዝገብ ቁጥር 259880

ህዳር 26 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች፡-----ሽመክት አሰፋ

አለማየሁ ሹናራ

ተናኜ ጥላሁን

ዋዚሞ ዋሲራ

ዘዉዲቱ ታደሰ

አመልካች፡-አቶ ሳሙኤል አሊ

ተጠሪ፡-1ኛ/ የአሶሳ ከተማ አስተዳደር መሬት ልማት ማኔጅመንት መምርያ

2ኛ/ የአሶሳ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጠ

**ፍርድ**

ለፍርዱ መነሻ የሆነው ክርክር ከይዞታ ጋር የተያያዘ የካሳ ጥያቄን መሰረት ያደረገ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በአሶሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት የተጀመረ ሲሆን የአሁን አመልካች ከሳሽ ሲሆኑ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡አመልካች በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ በአጭሩ፡-አመልካች በአሶሳ ከተማ ወረዳ 2 ቀጠና 2 ልዩ ስሙ ግብርና ሰፈር በሚባለው አከባቢ 10,000 (አስር ሺህ ) ካ.ሜ ይዞታ ከ1994 ዓ.ም ጀምሮ በእጄ አድርጌ የምጠቀምበት ያለዉና በይዞታዉ ላይ የብር 1,600,000/አንድ ሚሊዮን ስድስት መቶ

ሺህ ብር) የሚገመት ባህር ዛፍ፣ ማንጎ እና ጋርቭላ ያለው ሲሆን ተጠሪ ካሳ እና ምትክ ቦታ ሳይሰጠኝ ለ3ኛ ወገን አሳልፎ ስለሰጠብኝ ቅድምያ የማልማት መብቴ እንዲጠበቅልኝ፣ ምትክ መሬት እንዲሰጠኝ እና የአትክልቶቹ ካሳ ብር 1,600,000/አንድ ሚልዮን ስድስት መቶ ሺህ/ እንዲከፍል እንዲወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

በአመልካች አቤቱታ ላይ ተጠሪዎች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበው ፍ/ቤቱ ውድቅ አድርጎ ያለፈዉ ሲሆን በፍሬ ጉዳዩ ላይ ያቀረቡት መልስም ሲታይ፡- አከራካሪው ይዞታ አመልካች በወረራ

የተያዘ የአስተዳደሩ ሀብት ከመሆኑም በላይ አመልካች ያቀረቡት ማስረጃ ህገወጥ በመሆኑ ክሱ ዉድቅ ይደረግልን ሲሉ መልስ ሰጥቷል፡፡

በዚህ መልኩ ግራ ቀኙን ያከራከረዉ የአሶሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች ይዞታውን በህጋዊ መንገድ የያዙት ስለመሆኑ በማረጋገጥ የአመልካች ይዞታ ሆነዉን እና በላዩ ላይ አትክልት ያለዉን ሕጋዊ ይዞታ ተጠሪ ለልማት ብሎ ሲወስደዉ ለአመልካች ምትክ ቦታ ሳይሰጥ እና አትክልቶችን ግምት ሳይከፍል ተጠሪ በማህበር ለተደራጁ ወገኖች ያስተላለፈ ስለመሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ ተጠሪ ለአመልካች 400 ካ.ሜ የከተማ ምትክ ቦታ እንዲሰጠዉ እና የአትክልቱን ግምት ብር 468,130 .00 /አራት መቶ ስልሳ ስምንት ሺህ አንድ መቶ ሰላሳ ብር/ ለአመልካች እንዲከፍል በማለት እና ለአመልካች ቅድምያ የማልማት መብትን በመንፈግ ውሳኔ ሰጥቷል ፡፡

ተጠሪዎች በውሳኔው ቅር ተሰኝተው ለቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም አያስቀርብም በሚል ተሰርዟል፡፡

በመቀጠል ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው የሰበር ቅሬታ ለቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን የሰበር ችሎቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ለአመልካች 400 ካ.ሜ ምትክ ቦታ እንዲሰጠዉ የተባለዉን የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ ክፍል በማጽናት ቀሪዉን የአትክልት ካሳ ግምት ለአመልካች እንዲከፈል ሲባል የተሰጠዉን የውሳኔ ክፍል በመሻር ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡

ይህ ሰበር አቤቱታ የቀረበውም አመልካች በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ እንዲታረም በማለት ሲሆን የቀረበው የሰበር አቤቱታም አከራካሪው 10,000 ካ.ሜ ይዞታ የአመልካች ስለመሆኑ በሰው እና በሰነድ ማስረጃ ተረጋግጦ እያለ እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም 400 ካ.ሜ ምትክ ቦታ ለአመልካች እንዲሰጣቸው በማለት ወስኖ የአትክልቶችን ግምት እንዳይከፈል ሲል የተሰጠዉ የዉሳኔ ክፍል ስህተት ያለበት በመሆኑ እንዲታረምልኝ ሲል ጠይቋል፡፡

አመልካች ያቀረቡትን የሰበር ቅሬታ መነሻ ተደርጎ ካሳ የተጠየቀበት አትክልት ቦታ የአመልካች መሆኑ ተረጋግጧል በሚል በአሶሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተቀባይነት ያገኘውን ውሳኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ይዞታው የአመልካች መሆኑ አልተረጋገጠም በሚል የሻረበትን አግባብ ለሰበር ችሎቱ ከተሰጠው ስልጣን *አንጻር አግባብነቱን ለማጣራት ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪዎች መልሳቸውን ሰጥተዉበታል ፡፡*

ተጠሪ ያቀረቡት መልስም ይዘቱ ሲታይ፡- የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም ይዞታው በህገ ወጥ መንገድ የተያዘ ስለመሆኑ አረጋግጦ የክልሉ ካቢኔ ከአርሶአደሮች ጋር በደረሰው ስምምነት መሰረት 400 ካ.ሜ ለአመልካች ምትክ ይዞታ እንዲሰጥ ነገር ግን የአትክልት ግምት ካሳን በሚመለከት ሊከፈል አይገባም በማለት የሰጠው ውሳኔ አመልካች መብት በሌላቸው ይዞታ ላይ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ የስር ፍረድ ቤት ዉሳኔ የሚነቀፍ አይደለም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ቀደም ብሎ ከተያዘው ጭብጥ ዉስጥ አግባብነት ያለዉን ነጥብ ይህም የክልሉ ሰበር ችሎት ለአመልካች የአትክልት ግምት እንዲከፈለዉ ተብሎ የስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠዉን ዉሳኔ ለመሻር ስልጣን አለዉ ወይስ የለዉም የሚለዉን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

እኛም መዝገቡን መርምረን እንዳየነዉ የክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ የአመልካች ስለመሆኑ በማስረጃ መመዘን ስልጣን ያላዉ የአሶሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይዞታዉ ባለቤትነት ለማጣራት ምስክሮችን ሰምቶ፣ ከተለያዩ ተቋማት ከተዉጣጡ አካላት የይዞታዉን ባለቤት እንዲያጣራለት በማድረግ እና ስለ ይዞታዉ መግለጫ እንዲቀርብለት አድርጎ ይዞታዉም ሆነ በይዞታው ላይ ያሉ አትክልቶች የአመልካች ስለመሆናቸዉ በማረጋገጥ ተጠሪ ለአመልካች ምትክ ቦታ ሳይሰጥ እና ለአትክልቶቹ ግምት ሳይከፍል የአመልካችን ይዞታ ወስዶ ለ3ኛ ወገን ማስተላለፉ ተገቢነት የሌለዉ በማለት ተጠሪ ለአመልካች 400 ካ.ሜ ምትክ ቦታ እንዲሰጠዉ እና የአትክልቶቹን ግምት በሚመለከተው በባለሙያ ተጣርቶ የተረጋገጠዉን ብር 468,130.00 /አራት መቶ ስልሳ ስምንት ሺህ አንድ መቶ ሰላሳ ብር/ የአትክልት ግምት ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍል ሲል የተወሰነዉን እና ይህም በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያፀናዉን ዉሳኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ይዞታውን በሚመለከት የክልሉ መንግስት በወሰነው መሰረት 400 ካ.ሜ ምትክ ቦታ ለአመልካች እንዲሰጥ በማለት የተሰጠዉን ዉሳኔ ክፍል በማፅናት የአትክልት ግምት ብር 468,130.00 /አራት መቶ ስልሳ ስምንት ሺህ አንድ መቶ ሰላሳ ብር/ ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፈል ሲባል የተሰጠዉን ዉሳኔ ክፍል መሻሩን የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡

በዚህ ጉዳይ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን በተመለከተ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3) (ለ) ላይ በግልፅ እንደተቀመጠዉ በክልል ጉዳዮች በተሰጠ የመጨረሻ ዉሳኔ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ካለ ማረም እንዳለባቸዉ እንጂ በማስረጃ የተረጋገጠዉን ፍሬ ጉዳይን መርምረዉ ዉሳኔ መስጠት እንደማይችሉ የሚያሳይ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 55273 ላይ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎቶች ተጨማሪ ምስክሮች በመስማት እና ሌሎች ፍሬ ጉዳዮችን በማጣራት ማስረጃ በመመዘን ዉሳኔ ሊሰጡ እንደማይችሉ አስገዳጅ የህግ ትርጉም የተሰጠበት ሲሆን አሁን በእጃችን ባለዉ ጉዳይ ማስረጃ መመዘን ስልጣን ያላቸዉ

የአሶሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የክርክሩ መነሻ የሆነዉ ይዞታም ሆነ በይዞታዉ ላይ ያሉትን አትክልቶች ያለማዉ አመልካች ስለመሆኑ በማረጋገጥ 400 ካ.ሜ ምትክ ይዞታ ለአመልካች እንዲሰጠዉ እንዲሁም የአትክልቱን ግምት በባለሙያ በማጣራት ግምቱ የአመልካች እንዲከፈለዉ ተብሎ የተሰጠዉን ዉሳኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በጉዳዩ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለመኖሩ ሳይተነትን ወደ ፍሬ ጉዳዩ በመግባት በማስረጃ የተረጋገጠዉን በክሱ መነሻ በሆነዉ ይዞታ ላይ ያሉት አትክልቶች የአመልካች መሆናቸዉ ተረጋግጦ በክሱ መነሻ በሆነዉ ይዞታ ላይ ያለዉን የአትክልት ግምት ብር 468,130 .00 /አራት መቶ ስልሳ ስምንት ሺህ

አንድ መቶ ሰላሳ ብር/ ለአመልካች እንዲከፈል ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠዉን ዉሳኔ ክፍል የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መሰረታዊ የህግ ስህተት ማረም ሲገባዉ ይህን ተላለፎ ፍሬ ጉዳይ ዉስጥ በመግባት ያለምንም ሕጋዊ መሰረት የስር ፍርድ ቤቶች ለአመልካች የአትክልት ግምት ብር 468,130 .00 /አራት መቶ ስልሳ ስምንት ሺህ አንድ መቶ ሰላሳ ብር/ እንዲከፈል ተብሎ የተሰጠዉን ዉሳኔ ክፍል መሻሩ ያለ ስልጣኑ መሆኑን የተገነዘብን ስለሆነ ከዚህ አኳያ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ለአመልካች የአትክልት ግምት ሊከፈለዉ አይገባም ሲል የሰጠዉ የዉሳኔ ክፍል መሰረታዊ የህግ ሰህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡በመሆኑም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

- የቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/13081 ላይ በቀን 24/05/2016 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፌ/ጠ/ፍ/ቤት የሰበር ስነ ስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1)(ለ) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
- የቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/13081 ላይ በቀን 24/05/2016 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት ለአመልካች የአትክልት ግምት ሊከፈል አይገባም ሲል የሰጠውን ውሳኔ ክፍል በፌ/ጠ/ፍ/ቤት የሰበር ስነ ስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1)(ለ) መሰረት ተሽሯል፡፡
- ለአመልካች የአትክልት ግምት ብር 468,130 .00 /አራት መቶ ስልሳ ስምንት ሺህ አንድ መቶ ሰላሳ ብር/ ሊከፈለዉ ይገባል ተብሎ ተወስኗል፡፡
- የአሶሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 03252 ላይ በቀን 02/10/2015 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት የተሰጠዉ ውሳኔ እና የቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 12878 ላይ በጥቅምት 15 ቀን 2016 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የተሰጠዉ ዉሳኔ እንዲሁም የቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/13081 ላይ በቀን 24/05/2016 ዓ/ም በዋለዉ

ችሎት ለአመልካች ምትክ መሬት 400 ካ.ሜ ይሰጠዉ ሲል የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ በማፅናት የተወሰነዉ የዉሳኔ ክፍል በአግባቡ ስለሆነ በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ስነ ስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1)(ሀ) መሰረት ፀንቷል፡፡

- በዚህ ፍ/ቤት የወጣውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ ወገኖች ይቻቻሉ፡፡

## ትዕዛዝ

- በዚህ ችሎት የተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ ካለ እንዲነሳ ተብሎ ታዟል፡፡ይፃፍ
- የመዝገቡ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረሳቸው፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ዉሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መዝገብ ቁጥር - 260948

ቀን 30/03/2017 ዓ/ም-

ዳኞች - ሽመክት አሰፋ

እንዳሻው አዳነ

አለማየሁ ሹናራ

ተናኘ ጥላሁን

ዋዚሞ ዋሲራ

አመልካች፡ ዋረን ፋርማሲዮቲካል የጅምላ መድሀኒትና የህክምና መሳሪያዎች ድርጅት የቀረበ የለም

ተጠሪ - ኩሓ ጠቅላላ ሆስፒታል የቀረበ የለም

መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው ለምርመራ ስለሆነ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የተጀመረው በትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በኩሓ ክፍለ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች ከሳሽ የአሁን ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን የተከራከሩ ሲሆን ከሳሽ ያቀረቡት ክስ ይዘት ከተከሳሽ ጋር በ 28/08/2011 አ.ም የኬሚስትሪ ማሽን አቅርቦት በብር 985,000.00 (ዘጠኝ መቶ ሰማኒያ አምስት ሺህ ብር) ውል መፈፀማቸውንና በውሉ መሰረት ጥራቱን የጠበቀ የኬሚስትሪ ማሽን ያቀረብኩ ሲሆን ተከሳሽም ሶስት የላብራቶሪ ባለሞያ ኤክስፐርቶች ከጤና ጥብቃ ቢሮ፣ ከዓይደር ሆስፒታል የመጡ የህክምና መሳርያዎች ኤክስፐርቶች ባሉበት ብቃትና ጥራት ያለው መሆኑ እንዲሁም የተከሳሽ ሜዲካል

ዳይሬክተርም ማሽኑ በትክክል ጥራቱንና ብቃቱን አረጋግጦ ወደ ስራ መግባት እንዳለበት ወደ ስራ አስኪያጅ መርቶት ባለበት ሁኔታ ተከሳሽ ችግር ያለበት መሆኑን ሳያረጋግጥ ብሎም የላብራቶሪ ባለሞያ ጥራት የለውም ስላለ ውሉ እንዳይፈፀም እንቅፋት በመሆን ውሉን በመሰረዝ ገንዘብ እንዳየከፈለኝ ያገዱኝ ስለሆነ ተገደው በውሉ መሰረት ብር 985,000.00 (ዘጠኝ መቶ ሰማኒያ አምስት ሺህ ብር) እና ለወጪና ኪሳራ የዳረጉኝ በመሆኑ የጠበቃ አበልና የዳኝነት፣ ወለድ ሌሎች ወጪዎች እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ የሚል ዳኝነት ጠይቀዋል። ይህም ክስ ለተከሳሽ ደርሶ መልሳቸውን አቅርበዋል። የመልሳቸውም ይዘት ከሳሽ የጨረታው አሸናፊ በመሆን ጥራት ያለው ማሽን አቅርቢያለሁ ከማለት ውጪ ጥራት ያለው ማሽን መሆኑን አላረጋገጡም። ማሽኑ በባለሞያ ሲፈተሽ ስልሳ አይነት የላብራቶሪ ናሙና ውጤት መስጠት ሲገባው አስራ አንድ በመጀመሪያ በመቀጠል አራት ውጤት ብቻ በመስጠት የቆመ መሆኑ ከመረጋገጡም በላይ ማሽኑ ከውጭ ሲገባ መለዋወጫ፣ ኮምፒውተር፣ ፕሪንተር እና የማሽኑ ሶፍትዌር አብሮት መቅረብ ሲገባው ያልቀረበ በመሆኑ፣ ለማሽኑ ባለሞያ አሰልጥኖ ሰርተፊኬት መስጠት ሲገባው ይህንን ማድረጉን ያላረጋገጠና ማሽኑ በሞዴል 19 ገቢ ሆኖ በሞዴል 22 ወጪ ያልተደረገ ስለሆነ በግዥ መመሪያ 14/2007፣ በመድሀኒት ግዥ መመሪያ 13/2009፣ በአዋጅ ቁጥር 255/07 እና በውላችንን መሰረት የሚሰራ ማሽን ሳንረከብ ገንዘብ ለመክፈል፣ ቲኦቲ፣ የዳኝነት እና የጠበቃ ወጪ ልከፍል አይገባም ተብሎ በነፃ ከክሱ ልሰናበትና ወጪና ኪሳራ ብር 2,000 ከሳሽ ሊከፍል ይገባል ተብሎ ውሳኔ ይሰጥልኝ በማለት መልሳቸውን አቅርበዋል።

ፍርድ ቤቱም ከሳሽ በስፔሲፊክሽን መሰረት ዋስትና በመስጠት የጎደለ ካለ እንዲለውጥና እንዲያሟላ ጊዜ እንዲሰጠው በፅሁፍ የጠየቀና ተከሳሽ ግዴታውን በአግባቡ ሳይወጣ አልከፍልም ማለቱ አግባብነት የለውም በመሆኑም ተከሳሽ ለከሳሽ ብር 985,000.00 እና የባንክ ወለድ፣ የጠበቃ አበል፣ የዳኝነትና ሌሎች ወጪዎችን እንዲከፍል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል።

በዚህም ውሳኔ ቅር በመሰኘት የስር ፍርድ ቤት ተከሳሽ ወይም የአሁን ተጠሪ ለመቀሌ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ይግባኙ አያስቀርብም በማለት ሰርዞታል። በዚህም ቅር በመሰኘት የአሁን ተጠሪ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን በማከራከር ሁለት ጭብጦች የያዘ ሲሆን የጭብጦቹም ይዘት ተጠሪ በውሉ መሰረት ለክርክር መነሻ የሆነውን ማሽን ለአመልካች ማስረከቡን በማስረዳቱ ነው እንደ ክሱ የተወሰነለት? አመልካች ውል ይፍረስልኝ ማሽን ይቀየረልኝ ብሎ ስላልጠየቀ ግዴታህን አልተወጣህም ክፈል መባሉ በአግባቡ ነው? የሚሉ ጭብጦችን በመያዝ የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ በቀረቡት የሰውና የሰነድ ማስረጃ ማሽኑ በስፔስፊኬሽን መሰረት ያላቀረበ በማሽኑ ላይ የፍሪጅ ችግር፣ ሪኤጀንት ከሪየር ከመርፌ መውሰጃ ሪኤጀንት ጋር እንደሚጋጭ፣ የኮኔኬሽን ችግር እንዳለበት የተረጋገጠ በመሆኑ በ 28/10/11 ዓ/ም ለተጠሪ የተፃፈ በባዩ ሜዲካል ፍተሻ ከ 95% በላይ physical checkup ቢያልፍም እንኳ functionality cooling system gap፣ reagent carrier adjustment፣ communiction ክፍተቶች ያሉበት በሞዴል 19 ገቢ ያልሆነው ችግር ቢኖርበት በመሆኑ ተጠሪ በውሉ መሰረት ጉድለት በሌለበት አኳኋን ለአመልካች እንዳስረከበ ሳይረጋገጥና

የማረጋገጥ ግዴታውን ሳይዋጣ አመልካች እንዲከፍል መወሰኑ በአግባቡ አይደለም፡፡ ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ ተጠሪ ማሽኑ ለተፈለገበት አላማ እንዲውል ጥራቱን አሟልቶ ያላቀረበ በመሆኑ ለውሉ ማፍረሻ ምክንያት ስለሆነ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1815 መሰረት ውሉ የፈረሰ ስለሆነ ተከራካሪ ወኖች ወደ ነበሩበት መመለስ የሚገባቸው ስለሆነ ተጠሪ ኬሚስትሪ ማሽኑን አንስቶ ከመውሰድ ውጭ ከአመልካች የሚከፈለው ብር 985,000 የለም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህም ውሳኔ ቅር በመሰኘት የአሁን አመልካች በቀን 02/07/2016 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም አመልካች ያቀረብኩት ማሽን ጥራትና ብቃቱ ተረጋግጦ ወደ ተጠሪ ድርጅት የቀረበ ንብረት እንደሆነ በፍሬ ነገር ደረጃ መረጋገጥ ያለበት ሆኖ እያለ ሰበር ችሎት ግን የማይገባ ትንተና በመስጠት ንብረቱ ብቃትና ጥራት የሌለው በመሆኑ በሞዴል 19 ገቢ አልሆነም በማለት የማሽኑን ዋጋ ተጠሪ መክፈል የለበትም ብሎ ውሳኔ መስጠቱ መሰረታዊ የህግ ምዘና ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡ ይህ የማይገባ ከሆነ ማሽኑ በሌላ ገለልተኛ ባለሞያ አቅርቦ እንዲያረጋግጥ እና በተረጋገጠው መሰረት ተጠሪ ክፍያውን ሊፈፅም ሲገባ ሰልጣኞች ብቃት የለውም ስላሉ ብቻ ክፍያው ሊፈፀም አይገባም መባሉ በአግባቡ ባለመሆኑ የክልል ሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ ተሽሮ በገለልተኛ ባለሞያ ተረጋግጦ እንዲወሰን በነጥብ እንዲመለስልኝ፡፡ የክልል ሰበር ችሎት በውሳኔው ላይ የኮምንኬሽን ክፍተት፣ ሪኤጀንት ኬሬርና ኩሊንግ ሲስተም ጉድለት ነበረበት የተባለው ሰበር ችሎት የማይገባ ትንተና በመውሰድ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የማስረጃ ምዘና ስህተት ያለበት በመሆኑ ተሽሮ በወረዳና በዞኑ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ፀንቶ ተጠሪ በውሉ መሰረት የማሽኑ ዋጋ 985,000.00 (ዘጠኝ መቶ ሰማንያ አምስት ሺ ብር) ከወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፍሉ ውሳኔ ይሰጠኝ በማለት አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የቀረበውን የሰበር ቅሬታ ከስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔና ከተገቢው ህግ ጋር አጣምሮ በመመርመር በአብላጫ ድምፅ የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሥር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ሲሽር ማስረጃ በመመዘን የወሰነ መሆን አለመሆኑን እና ማስረጃ በመመዘን ወስኗል ቢባል ሥልጣን ያለው መሆን አለመሆኑን፤ እንዲሁም ማሽኑ የጥራትም ሆነ አክሰሰር ጉድለት መኖር አለመኖሩ በገለልተኛ ባለሙያ ተጣርቶ የተወሰነ መሆን አለመሆኑን ከውላቸውና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች አንጻር አጣርቶ ለመወሰን ያስቀርባል የተባለ በመሆኑ ይህም ለተጠሪ የደረሳቸው ሲሆን ተጠሪም በቀን 04/08/2016 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡

የመልሳቸውም ይዘት አመልካችና ተጠሪ በቀን 25/08/2011 ዓ.ም ባደረግነው አንቀፅ 1 እና 6 መሰረት ጥራቱ የተረጋገጠ ማሽን ማቅረብ ሲገባው ማሽኑ ላይ 60 ሙከራ ተደርጎ በመጀመሪያው 11 ቀጥሎ 4 ከሰራ በኃላ ማሽኑ መስራት አለመቻሉን በ 9 የላብራቶሪ ባለሞያዎች በመረጋገጡ፣ የማሽኑ ሶስት መለዋወጫዎች (አክሰሰሪዎች) የጎደለና ይህንንም አመልካች ያልካደ በመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም በቅፅ 17 በመዝገብ ቁጥር 89676 የማስረጃ ምዘና ስህተት መሰረታዊ የህግ ስህተት መሆኑን

አስገዳጅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በመሻር ውሳኔ መስጠቱ በአግባቡ እንጂ በሌለው ስልጣን ማስረጃ በመመዘን አይደለም፡፡ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሁለተኛ ደረጃ የተያዘው ጭብጥ በስር ፍርድ ቤት ያልተነሳ እና በተከራካሪ ወገኖች ክርክር ያልተደረገበት ጉዳይ ስለሆነ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ አንቀፅ 329(1) መሰረት ውድቅ እንዲደረግ ውድቅ ሊሆን አይገባም የሚባል ከሆነ አመልካች እና ተጠሪ ባደረግነው ውል አንቀፅ 6 ጥራቱ በባለሞያ የተረጋገጠና የተሟላ ማሽን ካልቀረበ ክፍያው እንደማይፈፀም እንጂ በገለልተኛ ባለሞያ ይረጋገጥ የማይል በመሆኑ በገለልተኛ ባለሞያ የሚረጋገጥበት አግባብ የሌለ በመሆኑ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ ፀንቶ ወጪና ኪሳራ ከመቻለ ወደ አዲስ አበባ በመመላለስ ለትራንስፖርት፣ ለአልጋ፣ ለምግብ ወዘተ ካወጣነው ውጪ ጋር ውሳኔ ሊሰጠኝ ይገባል በማለት መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡ ይህም ለተጠሪ ደርሷቸው በቀን 29/08/2016 አ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ የሰበር ቅሬታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ በተገለፀው መሰረት በመጠቃለሉ እኛም ለሰበር ቅሬታ መነሻ የሆነው ፍርድ የግራ ቀኙን ክርክር እና ከማስቀረቢያ ነጥብ አንፃረው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ማስረጃ የመመዘን ስልጣን መኖር አለመኖሩንና ለክርክሩ መነሻ የሆነው በአመልካች የቀረበው ማሽን የጥራት ጉድለት መኖሩ በገለልተኛ ባለሞያ ተረጋግጦ የተወሰነ መሆን አለመሆኑን በጭብጥነት በመያዝ አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች አገናዝበን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

መርምረን እንደተረዳነው ከሆነ የአመልካች ክርክር በውላችን መሰረት ማሽኑን አቅርቢያለሁ ገንዘቡን ሊከፍለኝ ይገባል የሚል ሲሆን ተጠሪ አመልካች ያቀረበው ማሽን በውላችን መሰረት ጥራቱን የጠበቀ አይደለም፡፡ ጉድለት ስለተገኘበት ገንዘቡን አልከፍልም በማለት ይከራከራል፡፡ በአመልካችና ተጠሪ መካከል የግዥና ሽያጭ ውል ላይ አመልካች ጥራቱን የጠበቀ ማሽን ለማቅረብ ተጠሪም ገንዘብ ለመክፈል መስማማታቸው አከራካሪ አይደለም፡፡ አከራካሪ የሆነው ጉዳይ በአመልካች በኩል የቀረበው የኬሚስትሪ ማሽን በስፔስፊኬሽን መሰረት አይደለም የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአመልካች በኩል የቀረበው የኬሚስትሪ ማሽን በውላቸው መሰረት ጥራቱን የጠበቀ አይደለም፡፡ የፍሪጅ ችግር፣ ሪኤጀንት ችግር፣ ከሪየር ከመርፌ መውሰጃ ሪኤጀንት ጋር የሚጋጭ መሆኑን የኮኔክሽን ችግር ያለበት መሆኑን ሌሎች ከማሽኑ ጋር አብረው መቅረብ የሚገባቸው ኮምፒውተር፣ ፕሪንተር እና የማሽን ሶፍትዌር አብሮ መቅረብ ሲገባ ያልቀረቡ መሆናቸውን በመጥቀስ ተጠሪ ገንዘቡን ሊከፍል አይገባም በማለት የደረሰበት ሁኔታ በእርግጥ የሰበር ስልጣን መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ማረም ቢሆንም ከማስረጃ ምዘና መርህ አንፃር ከላይ የተዘረዘሩት ጉድለቶች መኖራቸው ከተረጋገጠ ገንዘብ ተጠሪ እንዲከፍል መወሰን ከማስረጃ ምዘና መርህ አንፃር መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሚሆን ከዚህ አንፃር የክልሉ ሰበር ማስረጃ የመዘነበት ሁኔታ ያልተሰጠ ስልጣን ነው ሊባል አይችልም፡፡ በአመልካች በኩል የቀረበው እቃ የጥራት ጉድለት ያለበት መሆኑ በግራ ቀኙ በኩል ከቀረቡት ምስክሮች ውጪ በሌላ ገለልተኛ አካል ተረጋግጧል ወይ? ለሚባለው ጉዳይ በሌላ ገለልተኛ አካል አለመረጋገጡን ተጠሪም አልካደም የተጠሪ ክርክር ውላችን

የሚያስረዳው አመልካች ያቀረበው ማሽን ጥራት ደረጃው በባለሞያ ይረጋገጣል ይላል እንጂ በገለልተኛ ባለሞያ ስለማይል በገለልተኛ ባለሞያ ሊረጋገጥ አይገባም የሚል ነው፡፡ በእርግጥ በግራ ቀኙ መካከል ያላቸው ውል አመልካች ያቀረበው እቃ በባለሞያ ይረጋገጣል የሚል ቢሆንም በአመልካች በኩል የቀረበው ባለሞያ እቃው የጥራት ጉድለት የሌለበት መሆኑን ሲያስረዱ የተጠሪ ሆስፒታል ላብራቶሪ ባለሞያዎች የቀረበው ማሽን የጥራት ጉድለት ያለበት መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

የግራ ቀኙ ምስክሮች ለየራሳቸው የሚመሰክሩ ከሆነ ፍርድ ቤቱ ሌላ ገለልተኛ አካል እንዲያጣራ አድርጎ መወሰን ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ አስፈላጊ ነው፡፡ ሻጩ ያስረከበው ነገር እንደ ውሉ ትክክል መሆኑንና ጉድለትም የሌለበት ለመሆኑ ለገዥው አላፊ እንደሆነ በፍ/ብ/ህ አንቀፅ 2287 ስር ተደንግጓል፡፡ የሸጠው ነገር ለደንበኛው አገልግሎት ወይም በንግድ ረገድ ለመጠቀሚያ ጥሩነት የሌላቸው ሲሆን ሽያጭ ለገዥ ዋቢ እንዲሆን የፍ/ብ/ህ አንቀፅ 2289 ስር ተደንግጎ ይገኛል፡፡ አሁን በያዝነው ጉዳይ አመልካች ያቀረበው እቃ ጉድለት ያለበት መሆኑ በተጠሪ በኩል በቀረበው ማስረጃ ቢረጋገጥም የተጠሪ ማስረጃ ገለልተኛ ሆኖ የሙያ ቃል ሰጥቷል ለማለት የሚያስደፍር  ባለመሆኑ ከአመልካች በኩል የቀረበው የኬሚስትሪ ማሽን በሌላ ገለልተኛ ባለሞያ ቢረጋገጥ ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ አስፈላጊ ከመሆኑም ሌላ ፍትህ እንዳይዛባ የሚያደርግ ስለሆነ እቃው በሌላ ገለልተኛ ባለሞያ ሊረጋገጥ ይገባል ብለናል፡፡

ሲጠቃለል አመልካች ያቀረበው ማሽን የጥራት ጉድለት መኖር አለመኖሩ በሌላ ሆስፒታል ውስጥ በሚገኙ ባለሞያዎች ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባ በመሆኑ በከተማ ውስጥ ካሉት ሌሎች የመንግስት ሆስፒታል ባለሞያ ተረጋግጦ አስፈላጊ ከሆነ ሌሎች ተጨማሪ ማስረጃዎች ቃል ሰምቶ ሊወሰን የሚገባ ሆኖ አግኝተናል፡፡ ስለዚህ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጠው ፍርድ ከማስረጃ ምዘና መርህ አንፃር መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. የኲሓ ክፍለ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 07270 በቀን 13/09/2012 ኣ.ም፣ የመቀሌ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 31075 በቀን 29/01/2016 ኣ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እና የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 2013/2300 በቀን 17/04/2016 ኣ.ም የሰጠው ማስረጃ ምዘና መርህ አንፃር መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስነ ስርአት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9(1)(ለ) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ከላይ በፍርድ ሀተታ ላይ በተዘረዘረው መሰረት ከተጠሪ ሆስፒታል ውጪ ሌላ የመንግስት ሆስፒታል ውስጥ የሚሰሩ ባለሞያዎች በአመልካች በኩል የቀረበው የኬሚስትሪ ማሽን ጥራት እንዲያጣራ በማድረግ አስፈላጊ ከሆነ ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ይመች ዘንድ ሌላ ተጨማሪ ማስረጃ

ቃል በመስማት ተገቢ የሆነ ውሳኔ የኩሓ ክፍለ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤቱ እንዲወስን የሰበር ስነ ስርአት መመሪያቃ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9(2) መሰረት መልሰናል፡፡

3. በፍርዱ መሰረት እንዲፈፅም የውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻቻሉ፡፡
5. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ እግድ ካለ ተነስቷል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
## የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መ/ቁ 261424

ህዳር 24 ቀን 2017 ዓ/ም

ዳኞች - ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርቅነሽ እሱባለዉ

አመልካች ፡- አቶ ናሁሰናይ አጥናፉ   አልቀረቡም

ተጠሪ ፡- ኢትዮቴሌኮም ማዕከላዊ ሰሜን ሪጅን ነ/ፈጅ  ሄዋን ጌታቸው ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከለታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

### ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ የስራ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረዉ በአማራ ክልል ደብረ ብርሃን ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉም አመልካች ይግባኝ ሰሚው የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 0140470 ግንቦት 04 ቀን 2015 ዓ/ም የሰጠዉን ዉሳኔ እና የአ/ብ/ክ/መ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ ቁጥር 128765 ጥር 28 ቀን 2016 ዓ/ም የሰጠዉን ዉሳኔ በመቃወም መጋቢት 16 ቀን 2016ዓ/ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸዉ ነዉ፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው ተጠሪ በአመልካች ላይ ከስራ ደረጃ እና ደመወዝ ዝቅ በማድረግ የዲስፕሊን እርምጃ ወስዷል፡፡ ይህን ተከትሎ አመልካች ለወረዳው ፍርድ ቤት ባቀረቡት አቤቱታ በሌለሁበት ወቅት በተዘጋጀ የስራ ዝርዝር መሰረት ጨረታ ወጥቶ የጨረታ አሸናፊ ተለይቶ ከተቋራጩ ጋር የግንባታ ዉል ተይዞ ስራዉ ከተሰራ በኃላ በጨረታ ክፍያ ወቅት ከድንጋይ ግንብ ጋር በተያያዘ በስራዉ ዝርዝር ላይ

ሜትር ኩዩብ (m³) መሆን ሲገባዉ ሜትር ካሬ (m²) በመሆኑ የዋጋ ልዩነቱ ለተጠሪ ደርሶት እያለ እኔ በሌለሁበት የተሰራዉን ስራ በቅድሚያ ዉል ድርድር ወቅት፣ በዉሉ መፈረም ግዜ እና የመጀመርያ ክፍያ ወቅት ስህተቱን አይቶ ማስተካከል ይችል ነበር በማለት የዲሲፒሊን ቅጣት በመወሰን ከሱፐርቫይዘርነት የስራ ድርጃየ ዝቅ በማድረግ ከደመወዜ 10% በመቀነስ ለወደፊት ለደረሰዉ ጉዳት በህጉ አግባብ ብር 214,145.00 (ሁለት መቶ አስራ አራት ሺ አንድ መቶ አርባ አምስት) ትከፍላልህ በማለት የሰጠዉ የዲሲፒሊን ቅጣት ተነስቶ በሱፐርቫይዘርነት የስራ ደርጃየ እንድቀጥል እና ከደመወዜ የተቀነሰዉ 10% እንዲመለስ፤ ለወደፊት እንድከፈል የተወሰነዉን ገንዘብ ልትከፍል አይገባም ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡

ተጠሪ በሰጠው መልስ የስራ ዝርዝሩ የወጣዉ በሌለሁበት ነዉ ይበል እንጂ የስራ ዝርዝሩ ከወጣ በኃላ የጨረታ ሰነድ የፋይናሻል ምዘና የሚደረገዉ በኮሚቴ ሲሆን በስሩ የሚገኝ ባለሙያ የእሱን የስራ ክፍል ወክሎ ተገኝቶ የነበር በመሆኑ፤ ሪፖርቱን ተቀብሎ ከማፅደቁ በፊት ምን እንደተሰራ የመጠየቅ ኃላፊነቱንም አልተወጣም፤ አመልካች የቅድመ ዉል ድርድር ላይ ተሳታፊ የነበር በመሆኑ በእያንዳንዱ ነጠላ ዋጋ ዝርዝር ድርድር የሚደረግበት በመሆኑ በዚህ ጊዜ ስህተቱን ማረም የነበረበት እና ስህተቱን ባለማረሙ ጉዳት የደረሰብን በመሆኑ ስለ ስህተቱም አመልካች በኢሜል ያመነ በመሆኑ የዲሲፒሊን ቅጣቱ ተገቢ ነዉ ተብሎ ክሱ ዉድቅ ይደረግልን በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የደብረ ብርሃን ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በፍሬ ጉዳዩ ላይ የግራቀኙን ክስ እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ ለዲሲፒሊን ዉሳኔዉ ምክንያት የሆነዉ ስህተት የተፈፀመዉ አመልካች በሌለበት በዝውውር ሳይመጣ የተሰራ ስራ በመሆኑ፤ ውል ተደርጎ ስራው እየተሰራ በመሆኑ አመልካች በደረሰበት ሊያስተካክለው የሚችል አይደለም ፤ አመልካች በሌለበት ለተሰራ ስራ በዲሲፒሊን መጠየቁ ተገቢ ባለመሆኑ የዲሲፒሊን ውሳኔው ሊሰረዝ ይገባል በማለት ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝቶ ይግባኝ ለሰሜን ሸዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱ በቀረበዉ ይግባኝ አቤቱታ ላይ ግራቀኝን አከራሮ የስራ ዝርዝሩ የተሰራዉ አመልካች በሌለበት ግዜ ቢሆንም አመልካች ስለ ስራዉ ተጫራቾች ባቀረቡት ሰነድ የፋይናንሻል ምዘና በሚደረግበት ወቅት፣ ከጨረታ አሻናፊዉ ጋር ዉል ሲፈርም፣ እና ለተቋራጩ ሳይት ሲያስረክብ ስለተፈጠረዉ ስህተት ማወቅ የነበረበት እና ስለ ስህተቱም የሚያዉቅ መሆኑን በኢሜል የገለፀ በመሆኑ ተጠሪ ለደረሰበት ጉዳት አመልካች ላይ የወሰደዉ የዲሲፒሊን ቅጣት ተገቢ ነዉ፤ ተጠሪ በአመልካች ላይ ያሳለፈው የዲስፕሊን ቅጣት ውሳኔ ሊነሳ አይገባም በማለት የወረዳውን ፍርድ ቤት ያሳለፈውን ዉሳኔ ሽሯል፡፡

አመልካች በዚህ ዉሳኔ ላይ ለአ/ብ/ክ/መ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ችሎቱ በቀረበዉ አቤቱታ ላይ ግራቀኝን ካከራከረ በኃላ የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ አጽንቷል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

የሰበር አቤቱታው ለዚህ ፍርድ ቤት የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች መጋቢት 16/2016 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ በውሳኔው ተፈፀመ የሚሉትን ስህተት በመዘርዘር እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ ቅሬታው ተመርምሮ የድሲፐሊን ኮሚቴው ውሳኔ የካሳ ጉዳይን ጭምር የወሰነ መሆኑን ክርክሩ የሚያሳይ ሲሆን የወረዳዉ ፍርድ ቤት የዲሲፒሊን ኮሜቴዉ የሰጠዉን ዉሳኔ በመሻር ሲወስን እንዲሁም በየደረጃዉየሚገኙ የበላይ ፍርድ ቤቶችም የዲሲፒሊን ኮሚቴ የሰጠዉን ዉሳኔ በማፅናት የወሰኑ ከመሆኑ አንፃር የዲሲፒሊን ኮሚቴዉ የጉዳት ካሳ ጉዳይን የማየት እና የመወሰን ስልጣን የነበረዉ መሆን ያለመሆኑን አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ጉዳዩ ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪ መስከረም 21 ቀን 2017 ዓ/ም በተፃፈ መልስ አመልካች የስራ ኃላፊነቱን ባለመወጣቱ በድርጅቱ ላይ አለአግባብ የብር 214,145.00 (ሁለት መቶ አስራ አራት ሺ አንድ መቶ አርባ አምስት) ጉዳት ያደረሰ በመሆኑ  የዲሲፒሊን ኮሚቴ ጥፋቱን አረጋግጦ በአመልካች ላይ አስተዳደራዊ ቅጣት የወሰደ ሲሆን እርምጃዉ የህግ ጥሰት የሌለበት በመሆኑ ዉሳኔው ሊፀና ይገባል፤ አንድ ሰራተኛ የተሰጠዉን የስራ ኃለፊነት ባለመወጣቱ በአሰሪዉ ላይ ኢኮኖሚያዊ ጉዳት በሚደርስበት ግዜ አሰሪዉ በሰራተኛዉ ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ  የመዉሰድ መብት ያለዉ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች አስተዳደራዊ እርምጃዉ ተገቢ ነዉ በማለት የሰጡት ዉሳኔ የሚነቀፍ አይደለም፡፡ የዲሲፒሊን ኮሚቴዉ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጁን መሰረት አድርጎ በአሰሪና በሰራተኖች ማህበር የጋራ ስምምንት የተቋቋመ የሰራተኞች ጥቅም የሚያስጠብቅ ገለልተኛ ተቋም በመሆኑ የተወሰደዉ እርምጃ ተገቢ ነዉ ተብሎ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ እንዲፀና ይወሰንልን በማለት ተከራክሯል፡፡

አመልካች ጥቅምት 14/2017 ዓ.ም ባቀረቡት ተጠሪ የጉዳት ካሳን በተመለከተ የዲስፐሊን ኮሚቴው የማየት ስልጣን አለው የሚል መከራከሪያ ያላቀረበ በመሆኑ እና አመልካችን በዲስፐሊን ክስ ውሳኔ ተጠሪን ብር 214,145.00 (ሁለት መቶ አስራ አራት ሺ አንድ መቶ አርባ አምስት) እንዲያጣ ስላደረገ ተመላሽ እንደማደርግ ውሳኔ አስተላልፏል፤ የዲስፐሊን ኮሚቴው የዱዳት ካሳን የማየት ስልጣን የለውም ተብሎ ውሳኔወ ይሻርልኝ በማለት ቅሬታቸዉን አጠናክረዋል፡፡

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረው በዚህ ሁኔታ ሲሆን በበኩላችን ጉዳዩን መርምረናል፡፡ እንደሚታወቀው በህግ በሌላ ሁኔታ ተወስኖ የዳኝነት ስልጣን ለሌላ አካል ካልተሰጠ በቀር የካሳ ጉዳይን ጨምሮ በፍርድ ሊወሰን የሚገባው ጉዳይ ሊቀርብ እና ሊወሰን የሚገባው በፍርድ ቤት ነው፡፡ እንዲሁም የድሲፐሊን ጉዳዮችን ተመልክቶ በዲሲፐሊን ረገድ ውሳኔ ለመስጠት የተዘረጋው ስርዓት የፍትሐብሄር ጉዳዮች በመደበኛ ፍርድ ቤት ታይተው ከሚወሰኑበት ሥርዓት የተለየ ነው፡፡

ከፍርድ ቤት ውጪ ሌላ አካል የዳኝነት ስልጣን የሚኖረው ሥልጣኑ በህግ ሲሰጠው ነው፡፡ በዚህ መሰረት ህግ አውጭው አካል የዳኝነት ስልጣንን ለተለያዩ አካላት በግልፅ ህግ እንዲሰጥ እና እንደአግባቡ ሁኔታ የፍርድቤቶችን የቀጥታ የዳኝነት ስልጣን ፣ የይግባኝ የዳኝነት ስልጣን እንዲሁም የክለሳ

የዳኝነት ስልጣንን በሚያወጣው ህግ እንዲገድብ ወይም ጨርሶ እንዲያስቀር ይጠበቃል፡፡ በዚህ መልኩ በህግ ካልተወሰነ በቀር በህገ መንግስቱአንቀጽ 37 እና ስለ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ጠቅላላ ድንጋጌ በያዘው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ አንቀፅ 4 ሥር እንደተመለከተው ክስን ተቀብሎ በማከራከር ዳኝነት የመስጠት ሥልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች ብቻ ናቸው ፡፡ ስለሆነም የፍትሐብሄር የዳኝነት ሥልጣን በግልፅ ህግ ከፍርድ ቤቶች እጅ ሊወጣ መቻሉ አከራካሪ ባይሆንም ግልፅ ህግ በሌለበት ሁኔታ የድስፕሊን ኮሚቴ ከድሲፕሊን ጉዳዮች አልፎ የፍትሐብሔር ኃላፊነትን በተመለከተ በዳኝነት ሊወስን ይገባል የሚባልበት የህግ ምክንያት የለም፡፡

በተያዘውም ጉዳይ አመልካች በድሲፕሊን ኃላፊ ከተደረገበት ጉዳይ ጋር በተያያዘ ተጠሪ ብር 214,145.00 (ሁለት መቶ አስራ አራት ሺ አንድ መቶ አርባ አምስት) እንዲያጣ በማድረጋቸው የደረሰውን ጉዳት ሊክሱ (ገንዘቡን ተመላሽ) ሊያደርጉ ይገባል የሚለው ጉዳይ የፍትሐብሄር ክስ ቀርቦ ኃላፊነትና መጠኑም በዚሁ አግባብ ከሚወሰን በቀር ከድሲፕሊን ጉዳዩ ጋር ተያይዞ የሚወሰን አይደለም፡፡ አቤቱታው በመደበኛው የፍርድ ስርዓት እንዳይቀርብ የሚያስችል ሁኔታ ስላለመኖሩ እንዲሁም በድሲፕሊን ውሳኔው ይህ አለመካከተቱን መተመለከተ ተጠሪ ያቀረበው ግልጽ ማስተባበያ የለም፡፡ ፡

ስለሆነም የድሲፕሊን ኮሚቴው አመልካች ተጠሪን ብር 214,145.00 (ሁለት መቶ አስራ አራት ሺ አንድ መቶ አርባ አምስት) እንዲያጣ ስላደረገ ገንዘቡን ተመላሽ እንደሚያደርግ ያሳለፈው ውሳኔ ክፍል በፍርድ ታይቶ ዳኝነት ሊሰጥበት በሚገባ ጉዳይ ላይ ከዲስፕሊን ኮሚቴው ስልጣን ውጪ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ ሊታረም ይገባል ብለናል፤ የበላይ ፍርድ ቤቶችም ይህን ሳያርሙ ማለፋቸው የህግ ስህተት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. ተጠሪ ግንቦት 3/2015 ዓ.ም በአመልካች ላይ ያሳለፈው የዲስፕሊን ውሳኔ፤ እንዲሁም የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 0140470 ግንቦት 04 ቀን 2015 ዓ/ም የሰጠዉን ዉሳኔ እና የአ/ብ/ክ/መ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ ቁጥር 128765 ጥር 28 ቀን 2016 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2. ተጠሪ የዲሲፒሊን ቅጣት በመወሰን አመልካችን ከሱፐርቫይዘርነት የስራ ደርጃ ዝቅ በማድረግ ከደመወዝ 10% በመቀነስ ያሳለፈው ውሳኔ ሊነሳ አይገባም ተብሎ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡

3. ለደረሰዉ ጉዳት ብር 214,145.00 (ሁለት መቶ አስራ አራት ሺ አንድ መቶ አርባ አምስት) አመልካች ለተጠሪ ይከፍላሉ በሚል ከዲሲፒሊን ቅጣት ጋር ተያይዞ የተጠቀሰው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡

<u>ማስታወሻ</u>፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

4. ተጠሪ የደረሰውን ጉዳት አመልካች ሊክሱ (ገንዘቡን ተመላሽ) ሊያደርጉ ይገባል የሚል ቢሆን የፍትሐብሄር ክስ አቅርቦ ዳኝነት ሊጠይቅ ይገባል ብለናል፡፡
5. ዕግድ ካለ ተነስቷል፡፡
6. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
## የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 261799

ሕዳር 30 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሽመክት አሰፋ

አለማየሁ ሹናራ

ተናኜ ጥላሁን

ዋዚሞ ዋሲራ

ዘውዲቱ ታደሰ

አመልካች፡- ፀሐይ ኢንሹራስ አክሲዮን ማህበር - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ልጉዲ እርሻ ኃ/የተ/የግ/ማህበር - ጠበቃ አዲሱ ሀረገወይን - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች መጋቢት 20 ቀን 2016 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት ቅሬታ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 05250 በቀን 01/04/2016 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 319274 የካቲት 26 ቀን 2016 ዓ/ም በማጽናት የሰጠው ብይን መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት በመጠየቁ ነው፡፡

ጉዳዩ የንብረት ጉዳት ካሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁን ተጠሪ በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአሁን አመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ አመልካች በቀን

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

04/09/2015 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ ባቀረቡት ክስ የመድን ዋስትና ሽፋን የተሰጠው ንብረትነቱ በተጠሪ ስም የተመዘገበ የሠሌዳ ቁጥሩ ኮድ ኢት 3-77600 እና ኢት 3-23463 ዋና እና ተሳቢ ተሽከርካሪ በቤንሻንጉል ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት መተከል ዞን ጉባ ወረዳ ሆርሶ ቀበሌ ልዩ ቦታው ማንጁል ቡሾ በተባለ ቦታ ማንነታቸው ያልታወቁ ሽፍቶች ባደረሱት ጥቃት ከነተሳቢውና ከጫነው ጭነት ጋር ሙሉ ለሙሉ ሊወድም ችሏል፡፡ የአደጋው መንስኤ በመደበኛ የመድን ውሉ የተገለለ ቢሆንም ከሳሽ በተጨማሪ አረቦን ክፍያ የባንዲት፣ የሽፍታ እና ጎሬላ የመድን ሽፋን ለተሽከርካሪው ከነተሳቢው የተገባለት(sum insured) ብር 4,500,000.00(አራት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ብር) ነው፡፡ ተጠሪ አደጋውን በጊዜው ከማሳወቅ ጀምሮ ተገቢውን የኢንሹራንስ ሂደት ያሟላ ቢሆንም አመልካች አደጋው የመድን ሽፋን የለውም በሚል የከሳሽን የካሳ ጥያቄ ውድቅ ያደረገ በመሆኑ ብር 4,500,000.00 (አራት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ብር) ካሳ መክፈል ከሚገባው ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ፣ከወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

አመልካች በ07/10/2015 ዓ.ም በተጻፈ ባቀረቡት መልስ ተጠሪ ሊከፈለኝ ይገባል በማለት ያቀረቡት ጥያቄ በንብረቱ ላይ ከደረሰው ጉዳት መንስዔ ከመድን ፖሊሲው ጋር የማይገናኝ እና በማስረጃም ያልተደገፈ ነው፡፡ ተጠሪ የካሳ ክፍያ ሊከፈል ይገባል የሚለው ክሱ በተጨማሪ ጽሁፍ (Endorsement) አማካኝነት የባንዲት ፣ የሽፍታ ፣ እና ጎሬላ ሽፋን የገዛ መሆኑን በመግለጽ ሲሆን በፖሊሲው አንቀፅ 2.1 የተገለለ እና በተጨማሪ ሽፋን የተሰጠ ሲሆን በዚሁ መሠረት "armed or unarmmed robbery, armed or unarmed shifta action, holdup or any act of banditry" ያለትጥቅ ወይም በትጥቅ በታገዘ የንብረት ዝርፊያዎችና መሰል የአደጋ መንስዔዎች ለሚደርስበት ጉዳት የከሳሽ ንብረት ሽፋን ያገኘ ቢሆንም እነዚህ የአደጋ መንስዔዎች የንብረት ዝርፊያንና ቅሚያን የሚመለከቱ እና በመደበኛነት በአነስተኛ ክፍያ የሚሸፈኑ ሲሆን ተጠሪ ንብረት ላይ የደረሰው ጉዳት በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በወቅቱ የነበረው የፖለቲካና የጸጥታ ሁኔታ ጋር ተያይዞ በመሆኑ ተጠሪ ከመድን ሽፋን ውጭ ወይም በተገለለ መንስዔ በንብረቱ ላይ ለደረሰ ጉዳት ካሳ ይክፈለኝ በማለት ያቀረበው ክስ የውል እና የሕግ መሠረት የሌለው በመሆኑ የክሳ ጥያቄ ውድቅ ሊደረግ ይገባል፡፡ ሆኖም ግን ፍርድ ቤቱ ተከሳሽ ኃላፊነት አለበት የሚባልበት ምክንያት ካለ በውሉ አንቀጽ 4.5.1 እና በንግድ ሕግ ቁጥር 678 መሠረት አመልካች ሊከፈለው የሚገባው ዋስትና የተገባለትን የገንዘብ መጠን ሳይሆን ተሽከርካሪው/ተሳቢ አደጋ በደረሰበት ወቅት የነበረውን የገበያ ዋጋ የአደጋ መነሻ (Excess) 7% ተቀንሶ የተሽክርካሪውን ተሳቢ ቅሪት እና ንብረቱን

የሚመለከቱ ሕጋዊ ሰነዶች የማስረከብ እና ተከሳሽ በቅሪቱ ላይ ያለውን መብት ለመጠቀም ተገቢውን ውክልና የመስጠት ግዴታ ያለበትና አመልካች ከሰጠው ሽፋን ውጪ ወለድ የመክፈል ኃላፊነት የሌለበት ቢሆንም ኃላፊነት አለበት ቢባል እንኳን ፍቤቱ ውሳኔ ከሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የግራቀኙን ክርክር ከሰማ በኂላ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ተሽከርካሪ ላይ አደጋ የደረሰበት በባንዲቶች ፣ ሽፍቶች ወይም በሽምቅ ተወጊዎች ጥቃት አማካኝነት ነው? ወይስ በሌላ ምክንያት ነው? ተከሳሽ ከሳሽን የመካስ ኃላፊነት አለበት ? ወይስ የለበትም? አደጋ የደረሰበት ተሽከርካሪ ጉዳት በደረሰበት ጊዜ የወቅቱ ዋጋ ምን ያህል ነበር? የካሳ ክፍያው ገንዘብ ላይ ወለድ ሊታሰብ ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ በግራቀኙ የቀረቡትን የሰነድ ማስረጃዎችና ምስክሮቻቸውን ከሰማ በኂላ መዝገቡን መርምሮ በኢ.ፌ.ድ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 240(1) እና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት/ሰ/ሰሚ/ችሎት ሰ/መ/ቁ 209051 በተሰጠው የሽፍታ፣ ሽምቅነት ትርጓሜ፣ የተጠሪ ምስክሮች ጉዳቱን ያደረሱት የታጠቁ ሽፍቶች ከጫካ ወጥተው እንደሆነ እና ጉዳት ያደረሱት አካላት በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ሽፍታ መሆናቸው እንደሚታወቅ፤ እንዲሁም አደጋውን ያደረሱት ቡድኖች የታጠቁ ኃይሎች መሆናቸው በግራቀኙ የታመነ በመሆኑ በተጠሪ ተሽከርካሪ ላይ አደጋውን ያደረሱት ሽፍቶች ወይም ሽምቅ ተዋጊዎች መሆናቸውን በፍሬ ነገር ደረጃ ድምዳሜ ላይ በመድረስ አመልካች ጉዳት ለደረሰበት ተሽከርካሪ በሽፍትነት ወይም በትጥቅ ተዋጊነት እንቅስቃሴ ተግባር ላይ በተሰማሩ ቡድኖች ለሚደርስ አደጋ በመጀመሪያ መድን ፖሊሲ የተገለለ ቢሆንም በተጨማሪ ፖሊሲ የመድን ሽፋን የሰጠ በመሆኑ በተጠሪ ተሽከርካሪ ላይ የደረሰውን ጉዳት የመካስ ኃላፊነት አለበት፤

መጠኑን በተመለከተ በገባው ከሳሽ የወቅቱን ዋጋ ለማስገመት ፈቃደኛ ስላልሆነ የፖሊሲው ሽፋን መጠን የመድን እድሳት፣ የአደጋ መነሻ፣ ተቀናሽ ተደርጎ ብር 4,162,500 (አራት ሚሊዮን አንድ መቶ ስልሳ ሁለት ሺህ አምስት መቶ ብር) አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል፤ አመልካች ጉዳት የደረሰበትን ተሽከርካሪ አስመልክቶ ሊብሬ ጨምሮ ሌሎች ሰነዶችን ለተከሳሽ ማስረከብ ይኖርባቸዋል፤ አመልካች የተጠሪን የካሳ ጥያቄ ውድቅ ካደረገበት ከ22/01/2014 ዓ.ም ጀምሮ ከሳሽ ክስ እስካቀረቡበት 07/09/15 ዓ.ም የሚታሰብ ወለድ ብር 608,551.80 (ስድስት መቶ ስምንት ሺህ አምስት መቶ ሀምሳ አንድ ብር ከ 8/100) ፣ ወጪና ኪሳራ የጠበቃ አበልን ጨምሮ በድምሩ ብር 498,856 (አራት መቶ ዘጠና ስምንት ሺህ ስምንት መቶ ሃምሳ ብር) አመልካች ለተጠሪ ይክፈሉ በማለት ወስኗል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች ያቀረበው የሰበር ቅሬታም በተጠሪ ንብረት ላይ ጉዳቱ የደረሰበት ቦታ የብሔር እና መሰል የፖለቲካ አላማን ለማስፈጸም የሚንቀሳቀሱ አማጽያን በመንግሥት ላይ የጥቃት ድርጊቶችን በመፈፀም ሂደት የተጠሪን ብቻ ሳይሆን ብዙ ንብረቶችን ማውደማቸውንም በዚህም ምክንያት በቦታው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ (Marital Law) በሥራ ላይ ስለመዋሉ አረጋግጠን አቅርበን በፖሊሲው አንቀጽ 2.1 የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ (Marital Law) በሥራ ላይ እንዲውል ባስገደደ ማንኛውም ድርጊት ለደረሰ ጉዳት ኩባንያው በኃላፊነት እንደማይጠየቅ ተደንግጎ ባለበት እንዲሁም ዋናውን የመድን ውል ከክርክሩ ውጪ በማድረግ ውሳኔውን በተጨማሪ ጽሑፍ (Endorsements) የተራዘመ ሽፋን ላይ ብቻ መሠረት አድርጎ የተሳሳተ ትርጉም በመስጠት፤ በተጨማሪም የመድን ውል የሚሸፍነው ድርጊትን /ኹነትን ሆኖ እያለ ፍ/ቤቱ የደረሰው ጉዳት አድራሾቹ ማን ተብለው ይጠራሉ በሚል ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት የሌለውን ትርጓሜ በመስጠት የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የከፍተኛው ፍ/ቤት ይህን ውሳኔ ማረም ሲገባው አልፎ ማጽናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡ አመልካች በተጠሪ ንብረት ላይ ለደረሰው ሙሉ ውድመት ኃላፊነት አለበት ከተባለ ተጠሪ ቅሪቱን ካላስረከበ የካሣ መርህን (የንግድ ሕግ ቁጥር 678) እና የአመልካችን የመዳረግ መብት (ቁጥር 683) የሚጥስ ከመሆኑም በላይ በአመልካች የውል መብት (የፖሊሲው አንቀጽ 4.5.3) ላይ ጉዳት የሚያደርስ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፡፡ ወለድ መታሰብ ያለበት ውሳኔ ከተሰጠበት ወይም ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ መሆን ሲገባው ፍ/ቤቱ የካሳ ጥያቄው ውድቅ ከሆነበት ቀን አንስቶ መወሰኑ አግባብነት የለውም ፤ ተጠሪ ኪሣራ/ጉዳት የመቀነስ ግዴታ እያለበት ይህንን ግዴታውን ችላ ብሎ ቆይቶ ደረሰ የተባለውን ኪሣራ አመልካች እንዲከፍል መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ጠይቋል፡፡

የአመልካች ቅሬታ በሰበር ችሎት ተመርመሮ አመልካች ለተጠሪ በሰጠው የንግድ ተሸከርካሪዎች መድን ሽፋን በአንቀጽ 2.1 ከተገለሉት ውስጥ በተጨማሪ ስምምነት ከማግለያው እንዲወጡ ወይም ተጠሪ ሽፋን እንዲያገኙ ከተደረገው አንጻር ኃላፊነት አለበት በማለት የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ በተመለከተ በአመልካች የቀረበውን አቤቱታ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 28/1/ ድርጊቱ መድን ሽፋን የተሰጠበት ስለመሆኑ በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ በመሆኑ የአመልካች ቅሬታ ተገቢነት የለውም በማለት የሰጠውን ትዕዛዝ በዚህ ችሎት የሚኖረውን ውጤት

አመልካች ከሰጠው የመድህን ሽፋን አንጻር ኃላፊ ነው አይደለም የሚለውን እንዲሁም ቅሪተ አካሉን በተመለከተ በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ዳኝነት ቀርቦ በስር ፍ/ቤት የታለፈበትን አግባብ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንጻር ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲሰትበት ተደገርጓል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ መልስ የሰጠ ሲሆን ካቀረበው መልስ ጋር  የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበ ሲሆን ይኸውም በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 መሰረት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር  ችሎት  የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ በሚሰጠው ትዕዛዝ ላይ እንደገና የማየት (review) ስልጣን አልተሰጠውም፡፡ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ባለው ክርክር ሰበር አጣሪው በአንቀጽ 28 (1) መሰረት የመድን ሽፋንን እና ኃላፊነትን በተመለከተ አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ ተገቢነት የሌለው ነው በሚል ውድቅ በማድረግ የሰጠውን ትዕዛዝ የሰበር ችሎቱ እንደገና የሚያይበት አግባብ ስለሌለ ውድቅ ሊደረግ ይገባል፡፡ ተጠሪ ከመደበኛው ሽፋን ውጭ በተጨማሪ አረቦን ክፍያ ለተሽከርካሪው በወንበዴዎች፣ ሽፍቶች እና የደፈጣ ተዋጊዎች ለሚደርስ ማናቸውም ጥቃት የመድን ሽፋን የገባ በመሆኑ እና አደጋውም የደረሰው በነዚሁ አካላት መሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ ነው፤ የመድን ፖሊሲ ሊተረጎም የሚገባው በፍ/ህ/ቁ 1738(2) መሰረት ለተጠሪ ምቹ በሆነ መንገድ በሰፊው ነው፤ አመልካች ፖሊሲውን ከዝርፊያ ጋር ብቻ የተያዘ አስመስሎ ያቀረበው ክርክር የድርጊቱ ፈጻሚዎች ዓላማ ዝርፊያ እና ኢኮኖሚያዊ ብቻ መሆን አለበት በሚል ያቀረበው መከራከሪያ  ከመድን ውሉ ፅንስ ባህርይ ጋር የማይሄድ እና በመድን ፖሊሲው ላይ ያልሰፈረ ነው፡፡

በወቅቱ በቤንሻንጉል ክልል ውስጥ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የታወጀ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የለም፡፡ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ (state of emergy) በመደበኛ ውሉም ሆነ በባንዲት ሽፍታ እና ጎሬላ (BSG) የመድን ሽፋን አልተገለለም፤ በመደበኛው የንግድ ተሽከርካሪ የመድን ሽፋንም ቢሆን የተገለለው ወታደራዊ ህግን (matial law) የሚመለከት እንጂ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ (state of emergency) የሚመለከት አይደለም ፤ የመድን ሽፋን እንደ የፖሊሲው ባህርይ የድርጊቱን አድራሾች ማንነት ጭምር ሊያካትት ይችላል፡፡ ጉዳት የደረሰበት ተሽከርካሪ ሙሉ ለሙሉ በቃጠሎ የወደመ በመሆኑ ምንም ዋጋ የሚያወጣ ቅሪት ካለመኖሩም በላይ አመልካች ቅሪቱ ዋጋ አለው የሚሉ ከሆነ እንዲያስገምት በሥር ፍርድ ቤት ተጠይቀው የማስገመት ፍላጎት እንደሌላቸው ለችሎቱ አረጋግጠዋል፡፡ በመሆኑም ቅሪቱን ከአደጋው ቦታ የማንሳት ኃላፊነት የአመልካች በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች ለአመልካች መብት የሚሰጡ የተሽከርካሪውን ሰነዶች ተጠሪ እንዲያስረክብ እና አመልካች መብቱን እንዲጠቀም የሚያስችል ውሳኔ መስጠታቸው ምንም

ዓይነት መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሌለበት የቀረበውን የሰበር አቤቱታ ውድቅ ተደርጎ የሥር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ እንዲጸና ይወሰንልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተመለከተው ነው፡፡ ይህ ችሎትም ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ጭብጥ ከግራቀኙ ክርክር፣ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ የተፈጸመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካች አደጋ ለደረሰበት ተሽከሪካሪ በመጀመሪያ የሰጠው መድን ፖሊሲ ባንዲት፣ ሽፍታ እና ጎሬላን አግሎ የነበረ መሆኑንና በኋላ በተጨማሪ ባደረጉት ፖሊሲ ማካተታቸውን እንዲሁም አደጋውን ያደረሱት ቡድኖች የታጠቁ ኃይሎች መሆናቸው በግራቀኙ የታመነ ከመሆኑም በላይ በተጠሪ ተሽከርካሪ ላይ አደጋውን ያደረሱት ሽፍቶች ወይም የታጠቁ ኃይሎች መሆናቸው በማስረጃ ማጣራት እና ለመመዘን ሥልጣን ባለው በሥር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ  ተረጋግጦ ድምዳሜ ላይ የተደረሰበት መሆኑን ከውሳኔ ግልባጭ መረዳት ይቻላል፡፡

አመልካች የሚከራከረው በተጨማሪ የመድን ፖሊሲ ለባንዲት፣ ሽፍታ እና ጎሬላን በደን የተሰጠ ቢሆንም የብሔር እና መሰል የፖለቲካ አላማን ለማስፈጸም የሚንቀሳቀሱ አማጽያን በመንግሥት ላይ የጥቃት ድርጊቶችን በመፈፀም ሂደት የተጠሪን ንብረት ያወደሙ ስለሆነ ተራ ወይም መደበኛ ሽፍታ ስላልሆኑ የአደጋ ምክንያቱ ከመድን ፖሊሲ ውጭ ነው፤ ዋናውን የመጀመሪያውን ውል ወደ ጎን በመተው በተጨማሪ ውል ላይ መሠረት ተደርጎ መወሰኑ ስህተት ነው፤ በወቅቱ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ነበር፤ስለ ሽፍትነት በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ 209051 የተሰጠውን ትርጉም ፍርድ ቤቱ ያለአግባብ በመጥቀስ ወስኗል፡፡ቅርተ አካል እንድሰጠኝ ጠይቄ ውሳኔ ሳሰትበት መታለፉ አግባብ አይደለም በማለት ነው፡፡

በመሠረቱ ውል በፍብ/ሕግ ቁ.1731 እንደተደነገገው በሕጉ አግባብ የተቋቋሙ ውሎች ባቋቋሙዋቸው ሰዎች ላይ ሕግ ናቸው፡፡ ከሣሽ የሆነው ወገን ተጣሰብኝ የሚለውን መብት ማስከበር ዳኝነት የሚጠይቀው የመብቱን ምንጭ ወይም መሠረት ውል ወይም ህግ እንደሆነ በማረጋገጥ ስለመሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡

ውሌታዎች ግልጽ በሆኑ ጊዜ ዳኞች ግልጽ ከሆነው በመራቅ የተዋዋ ወገኖች ፈቃድ ምን እንደነበረ ለመተርጎም የማይችሉ እንደሆነ እና ትረጉም የሚያስፈልገው እንደሆነ ደግሞ በተዋዋዮቹ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

መካከል ሊኖር የሚገባውን የቅንነት እና የመተማመንን ግንኙነት መሠረት በማድረግና በጉዳዮቹ ውስጥ ያለውን ልማዳዊ ሥርዓት በመከተል በቅን ሊቦና ሊተርጎም የሚገባ ስለመሆኑ በፍብ/ሕግ ቁ.1732 እና ተከታዮቹ ተደንግጓል፡፡

ወደ ተዘው ጉዳይ ስንመለስ በሰበር ችሎት የተያዘው ጭብጦችን እንደሚከተለው እንመረምራለን፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ አመልካች ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ ነው ተብሎ ካሳ እንዲከፍል የተወሰነበትን ሰበር አጣሪ ችሎት ለሰበር ሊመራ አይገባም በማለት ውድቅ አድረጎ የሰጠበት ትዕዛዝ ለሰበር ችሎት ውጤቱ ምንድ ሊሆን ይችላል የተባለውን በተመለከተ የፌ/ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 28(1) ደንብ መውጣቱ እንደ ተተበቀ ሆኖ አቤቱታ በሰበር ችሎት የሚሰማው አስቀድሞ ሦስት የጠቅላ ፍረድ ቤት ዳኞች ለሰበር ችሎት መታየት አለበት ብሎ ሲወስን ነው በማለት በአስገዳጅ ሁኔታ የተደነገገ ሲሆን ይህንን አዋጅ ለማስፈጸ የወጣው የፌ/ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 እንቀጽ 6(1) ደግሞ የሰበር አቤቱታ ለሰበር ችሎት የሚቀርበው እና የሚሰማው አዋጁ አንቀጽ 28(1) መሠረት አቤቱታው አስቀድሞ የሰበር አጣሪ ችሎት አበቱታው የቀረበበት የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ከአዋጁ አንቀጽ 2(4) እና አንቀጽ 10(1) ሥር ከተመለከቱት ምክንያቶች አንፃር በሰበር ችሎት መታየት አለበት ብሎ ሲወስን ብቻ ነው በሚል አስገዳጅነቱ ጠበቅ ተደርጎ ተደንግጓል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች የምንረዳው የሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታውን የሚመረምረው በሰበር አጣሪ ችሎት ሲመራለት ብቻ እንደሆነ ነው፡፡ በሌላ በኩል ሙሉ በሙሉ ወይም በከፍል በአጣሪ ችሎት ሳይመራለት ቢቀረስ አቤቱታ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ ይችላልን ሰበር ችሎትስ ሊመረመረው አግባብነት አለውን የሚለው በግልጽ በህጉ ባይቀመጥም ከአዋጁ አንቀጽ 28(1) እና ከመመሪያ ቁጥር 17/2015 እንቀጽ 6(1) ድንጋጌዎች አንፃር ሲታይ በአጣሪ ችሎት ለተመራለትን ሰበር ችሎቱ ለመመርመር የማይችል መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም የንብረት ካሳ ኃላፊነት እና ካሳ ውሳኔውን በተመለከተ በመጀመሪያ መድን ፖሊሲ የተገለለ ቢሆንም በተጨማሪ ፖሊሲ ለባንዲት፣ ሽፍታ እና ጎሬላን የመድን ሽፋን የሰጠ መሆኑትን በማስረጃ በፍሬ ነገር ደረጃ በማረጋገጥ እና ሽፍታ ለሚለው ቃልም የተሰጠውን ትረጉም በማረጋገጥ አመልካች በተጠሪ ተሽከርካሪ ላይ የደረሰውን ጉዳት የመካስ ኃላፊነት አለበት በማለት ካሳ የወሰነበትን ክፍል አጣሪ ችሎት ያልመራበት ስለሆነ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ አልተለወጠም፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

በመጨረሻ ቅርተ አካሉን እንድሰጠን ዳኝነት ጠይቀን ሳይወሰን በዝምታ መታለፉ አግባብ አይደለም በሚል የቀረበውን የሰበር ቅሬታ በተመለከተ እውነትም አመልካች ዳኝነት ጠይቆ ውሳኔ ሳያርፍበት መታለፋን የውሳኔ ግልባጮች ያሳይሉ፡፡

በመሠረቱ በተከራካሪ ወገኖች የተጠየቀውን ዳኝነት አስመልክቶ ግልጽ ፍርድ አለመስጠት ስህተት ስለመሆኑ ፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ.39144 እና ሌሎች ተዛማጅ መዛግብት ላይ የሕግ ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች የተሽከርካሪውን ቅሪተ አካል እና ንብረቱን የሚመለከቱ ሕጋዊ ሰነዶች እና በቅሪተ አካሉ ላይ ያለውን መብት ለመጠቀም ተገቢውን ውክልና ተጠሪ እንዲሰጥ ዳኝነት ተጠይቆ ሳለ የሥር የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአግባቡ አጣርቶ ውሳኔ ሳያሳርፍበት ማለፉ፤ እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህንን ሳያርም በዝምታ ማለፉ በአግባቡ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2 (4/መ) እና 10(1/ሀ) መሠረት መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

ውሳኔ

1. የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 05250 በቀን 01/04/2016 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 319274 የካቲት 26 ቀን 2016 ዓ/ም በማጽናት የሰጠው ብይን በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 28(4) እና በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9 (1/ለ) መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. ቅርተ አካሉን በተመለከተ በአመልካች የቀረበው የዳኝነት ጥያቄ በዝምታ መታለፉ በአግባቡ ስላልሆነ ሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ እና በማስረጃ አጣርቶ እንዲወስን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.343/1 መሠረት መልሰናል፡፡
3. ሌላው የዉሳኔ ክፍል በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1/ሀ) መሠረት መሠረት አልተነካም፡፡
4. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡
5. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

**ማስታወሻ፡** - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

# በታህሳስ ወር 2017 የተወሰኑ

# 23 የሰበር ችሎት ውሳኔዎች

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መዝገብ ቁጥር - 242024

ቀን - 30/04/2017 ዓ.ም

ዳኞች - ሽመክት አሰፋ

እንዳሻው አዳነ

አለማየሁ ሹናራ

ዋዚሞ ዋሲራ

ዘውዲቱ ታደሰ

አመልካች - የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን

ተጠሪ - ብርሃን ባንክ አክስዮን ማህበር

መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው ለምርመራ ስለሆነ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በተጠሪ ላይ በስር ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ፍሬ ቃሉ በአጭሩ በከሳሽና በተክለ ብርሃን አምባዬ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማ መካከል የመንገድ ስራ ፕሮጀክት ውል መዋዋላቸውን ጥር 08 ቀን 2014 ኢ.ም ሰርቶ እንዲያጠናቅቅ መስማማታቸውን ነገር ግን ስራውን በውሉ መሰረት ባለመስራቱ ከሳሽ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ የስራ ውሉን ያቋረጠ መሆኑን ለተቋራጩ ቅድመ ክፍያ በሁለት ዙር 96,000.00 እና 43,600,173.83 የተከፈለ መሆኑን ተከሳሽ ለቅድመ

ክፍያ ዋስትና ብር 89,609,174.04 ለ 2 ዓመት ከ 5 ወር የሚቆይ ዋስትና የሰጠ መሆኑን ተከሳሽ የሰጠው የዋስትና አይነት ጥያቄ እንዳቀርብ የሚከፈል በመሆኑ ተከሳሽ የቅድመ ዋስትና ገንዘብ ብር 89,609,174.02 ከመስከረም 19 ቀን 2012 አ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍል የሚል ነው፡፡ ከተከሳሽ በኩል የተሰጠው መልስ ተክለብርሃን አምባዬ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማ ለሚሰራው የመንገድ ስራ ፕሮጀክት ስራው እስከ 80% ድረስ እስከደርስ ብር 89,609,174.02 የቅድመ ክፍያ ዋስትና የሰጡ መሆኑን በተቋራጩ የተሰራ ስራ መኖር ወይም አለመኖሩ ግምት ውስጥ ሳይገባ የዋስትና ገንዘብ እንዲከፍል መጠየቁ አግባብ አይደለም፡፡ ከሳሽ የተሰራው ስራ በማስላት ባልተመለሰ ገንዘብ ልክ መጠየቅ ሲገባው በተቋራጩ ምንም አይነት ስራ እንዳልተሰራ በመቁጠር በዋስትና ሰነድ የተጠቀሰውን የገንዘብ መጠን ሙሉ በሙሉ እንዲከፍል ሊጠየቅ አይችልም፡፡ ተቋራጩ ወደ ክርክር ውስጥ እንዲገባ ጠይቋል፡፡ በቃል ክርክር ጊዜ ተቋራጩ 1.83% ብቻ ሰርቶ የጠፋ ስለሆነ ወደ ክርክሩ እንዲገባ ሊፈቀድ አይገባም ሲል ከሳሽ ተከራክሯል፡፡ ተከሳሽ በበኩሉ የተሰራው ስራ ከ 38% በላይ በመሆኑ የቅድመ ዋስትና ገንዘብ ሙሉ በሙሉ እንዲከፍል መጠየቁ አግባብ አይደለም ሲል ተከራክሯል፡፡ የግራ ቀኙ የፅሁፍና የቃል ክርክር ከተጠናቀቀ በኃላ ጣልቃ ገብን ወደ ክርክሩ እንዲገባ መፍቀድ ጉዳዩን ማጓተት ይሆናል በማለት የተከሳሽን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ ተቋራጩ የሰራው ስራ አለ ወይስ የለም? ተቋራጩ የሰራው ስራ ካለ ከቅድመ ክፍያ ላይ ሊቀነስ ይገባል ወይስ አይገባም? ተከሳሽ ለከሳሽ ሊከፍል የሚገባው ገንዘብ ምን ያህል ይሆናል? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ መዝገቡን መርምሮ ተቋራጩ የሰራው ስራ ብር 2,723,343.08 መሆኑን ተቋራጩ የቅድመ ክፍያ ከወሰደ በኃላ የሰራው ስራ መኖሩ እስከተረጋገጠ ድረስ ተከሳሽ በሰጠው ዋስትና መሰረት ለከሳሽ ከሚከፍለው ገንዘብ ላይ ሊቀንስ ይገባል፡፡ ከሳሽ የተቋራጩ ሂሳብ ጉድለቱን ስለሚያሳይ የስራ ስራ ቢኖርም የሚቀንስ ገንዘብ የለም ማለቱ ስህተት ነው፡፡ በመሆኑ ተቋራጩ የሰራው ስራ መጠን ብር 2,723,343.00 እና በግናባታ ስራ ቦታ ላይ ያለው ንብረት ግምት ብር 836,303.80 በአጠቃላይ ብር 3,559,649.88 ተቋራጩ ከወሰደው ቅድመ ክፍያ ብር 89,609,174.14 ተቀንሶ የሚመጣው ብር 86049127.14 ተከሳሽ እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡ ወጪና ኪሳራ በቁርጥ 1,000.00 ብር እንዲከፍሉ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች ቅር በመሰኘት የይግባኝ ቅሬታ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ የቅሬታውም ይዘት ተቋራጩ የሰራው ስራ ከሳሽ በማስላት ተቀናሽ ሳያደርግ ሊጠይቅ አይገባም ማለቱ ስህተት ነው፡፡ የባንኩ ዋስትና ያለቅድመ ሁኔታ ጥያቄ እንደቀረበ የሚከፈል ገንዘብ ሆኖ እያለ ተቋራጩ የሰራው ስራ ተገምቶ ከቅድመ ክፍያ ገንዘብ መቀነሱ ስህተት ነው፡፡ በውላችን አንቀፅ 63(1) መሰረት በተቋሙ ጥፋት ውሉ ሲቋረጥ በግንባታ ቦታ ላይ

ያለው ንብረት አሰሪው በመጠቀም ያልተጠናቀቁ ስራዎች እንደሚያጠናቅቅ ተስማምተን እያለ በግንባታ ቦታ ያለው ንብረት ግምት ከሳሽ እንዲከፍል መደረጉ ስህተት ነው፡፡ ወለድ እንድከፍል ሳይወሰን መታለፉ ስህተት ነው፡፡ ፍርድ ቤቱም ተቋራጩ የሰራው ስራ ተገምቶ ከቅድመ ክፍያ ውስጥ እንዲቀንስ መደረጉና ወለድ ሳይወሰን መታለፉን ለማጣራት በማስቀረቡ ግራ ቀኙ ክርክር ካደረጉ በኃላ ተቋራጩ የሰራው ስራ ግምትና በግንባታ ሳይት የቀረው ንብረት ግምት ታስቦ ቀሪ የቅድመ ክፍያ ገንዘብ እንዲከፍሉ መወሰኑ በአግባቡ ነው፡፡ ወለድን በተመለከተ የብር 86,049,127.44 ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ገንዘቡ ተከፍሎ እስከሚጠናቀቅበት ጊዜ ድረስ ያለው ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር እንዲከፍሉ ሲል አሻሽሎ ወስኗል፡፡

የአሁን ሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ በተሻሻለው ውሳኔ ላይ አመልካች ቅር በመሰኘት ሲሆን የሰበር አቤቱታ ይዘቱም በአጭሩ ተጠሪ የሰጠው የዋስትና አይነትና ባህሪ ያለ ቅድመ ሁኔታ የክፍያ ጥያቄ እንደቀረበ የሚከፈል የባንክ ዋስትና ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤቶች ተቋራጩ የስራ ሥራ ግምትና በግንባታ ቦታ የቀረው ንብረት ግምት በማስገመት ከቅድመ ዋስትና ገንዘብ እንዲቀነስ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፡፡ በውላችን ጠቅላላ ሁኔታ አንቀፅ 63(1) ስር በተቋራጩ ጥፋት ውሉ ሲቋረጥ በግንባታ ቦታ ያለውን ንብረት በመጠቀም አሰሪው ቀሪ ስራ ያሰራል ስለሚል በግንባታ ቦታ ያለው ንብረት ግምት አመልካች እንዲከፍል ማድረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ ተጠሪ ያለ ቅድመ ሁኔታ የክፍያ ጥያቄ እንደቀረበ ለመክፈል በሰጠው ዋስትና መሰረት ጠቅላላ የዋስትና ገንዘብ ብር 89,609,174.02 የክፍያ ማስታወቂያ ከተሰጠበት ከ 19/01/2012 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍል እንዲወሰን የሚል ነው፡፡ አጣሪ ችሎት ተጠሪ የክርክር መነሻ ለሆነው የመንገድ ስራ ፕሮጀክት የሰጠው የዋስትና ሰነድ ያለቅድመ ሁኔታና የክፍያ ጥያቄ እንደቀረበ የሚከፈል ስለመሆኑ በተገለፀበት ክፍያው ሊከፈል የሚገባው የተሰራው ስራ መጠንና የመሳሪያ ግምት ሂሳብ ተቀናሽ ተደርጎ ለአመልካች ሊከፈል ይገባል በሚል የተወሰነበት አግባብነት ከሰበር መዝገብ ቁጥር 168954፣ 191402 እና ተዛማጅ ነጥቦች አንፃር ለማጣራት ሲባል ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ የበኩሉን መልስ በ 21/09/2015 ዓ.ም 06 ገፅ አቅርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡ ይዘቱ በአጭሩ በተቋራጩ የተሰሩ ስራዎች እና በሳይት ቦታ የቀሩ ንብረቶች ግምት ተገምቶ ተጠሪ ከሰጠው ቅድመ ክፍያ ዋስትና ገንዘብ እንዲቀነስ መወሰኑ በአግባቡ ስለሆነ የአመልካች ቅሬታ ውድቅ ተደርጎ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲፀናልኝ የሚል ነው፡፡ አመልካች የመልስ መልሱን በ 25/09/2015 አ.ም 06 ገፅ ሰበር ቅሬታውን በማጠናከር አቅርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ በተገለፀው መሰረት የተጠቃለለ በመሆኑ እኛም ለሰበር ቅሬታ መነሻ የሆነውን ፍርድ፣ የግራ ቀኙን ክርክር ከማስቀረቢያ ነጥብ አንፃር ተጠሪ የሰጠው የቅድመ ክፍያ ዋስትና ያለ ቅድመ ሁኔታ የሚከፈል ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ ይዘን ከሰበር መዝገብ ቁጥር 168954 እና 191402 አንፃር አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር አገናዝበን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

መርምረን እንደተረዳነው ከሆነ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ከተክለ ብርሃን አምባዬ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማ ጋር የመንገድ ስራና ፕሮጀክት ውል መግባቱን በውሉ መሰረት ስራውን ሰርቶ ባለማጠናቀቁ ውሉ የተቋረጠ ስለሆነ በሁለት ዙር ቅድመ ክፍያ ለተቋራጩ መከፈሉን ተከሳሽ ለቅድመ ክፍያ በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ ዋስትና ብር 89,609,174.02 (ሰማኒያ ዘጠኝ ሚሊዮን ስድስት መቶ ዘጠኝ ሺህ አንድ መቶ ሰባ አራት ብር ከዜሮ ሁለት ሳንቲም) ዋስትና የሰጠ በመሆኑ ይህን ገንዘብ ከመስከረም 19 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍል እንዲወሰን የሚል ነው፡፡

ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስ ተቋራጩ ተክለብርሃን አምባዬ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማ የሰራው ስራ እና በግንባታ ሳይት ቦታ ያለው ንብረት ታስቦ ከተጠየቀው ገንዘብ ውስጥ ሊቀነስ ይገባል እንጂ ሙሉ በሙሉ ሊካፈል አይገባም ሲል ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን የያዘው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተክለብርሃን አምባዬ ኮንስትራሽን ኃ/የተ/የግ/ማ የሰራው ስራ እና በግንባታ ቦታ ላይ የቀረው ንብረት በባለሞያ እንዲገመት ካደረገ በኃላ የተሰራው ስራ ግምትና በግንባታ ቦታ ላይ ያለው ንብረት ግምት ብር 3,559,649.88 (ሶስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሃምሳ ዘጠኝ ሺህ ስድስት መቶ አርባ ዘጠኝ ብር ከሰማኒያ ስምንት ሳንቲም) ተቀንሶ ብር 86,049,127.14 (ሰማኒያ ስድስት ሚሊዮን አርባ ዘጠኝ ሺህ አንድ መቶ ሃያ ሰባት ብር ከአስራ አራት ሳንቲም) እንድከፍል ወለድን በተመለከተ ተከሳሽ ሊከፍል አይገባም ወጪና ኪሳራ በቁርጥ 1,000.00 (አንድ ሺህ ብር) እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባን ሰሚ ችሎት በግንባታ ቦታ የቀረው ንብረት ግምት ብር 836,303.80 (ስምንት መቶ ሰላሳ ስድስት ሺህ ሶስት መቶ ሶስት ብር ከሰማኒያ ሳንቲም) እና በተቋራጩ ውሉ እስከ ተቋረጠበት ጊዜ ድረስ የተሰራው ስራ ብር 2,723,343.08 (ሁለት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሃያ ሶስት ሺህ ሶስት መቶ አርባ ሶስት ብር ከስምንት

ሳንቲም) መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች ተጠሪ የሰጠው ዋስትና ያለ ቅድመ ሁኔታ የክፍያ ጥያቄ እንደቀርብ የሚከፍል በመሆኑ የቅድመ ክፍያ ዋስትና ገንዘብ ሙሉ በሙሉ እንዲከፍል በማለት ያቀረበው ጥያቄ ያለቅድመ ሁኔታ ነው የሚለው ስምምነት ለተሰራ ስራ ሂሳብ ተቀናሽ አይደረግም ማለት ሳይሆን ከስራ ውጭ ለሚያጋጥም በሌላ ምክንያት ሊያዝ አይገባም ለማለት ነው የሚል ትርጉም በመስጠት የተሰራው ስራ እና በግንባታ ቦታ ለቀረው ንብረት ግምት እንዲቀነስ መወሰኑ በአግባቡ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በማፅናት ወለድን በተመለከተ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በመሻር ወለድ ከየካቲት 16 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር ተጠሪ እንዲከፍሉ ሲል ወስኗል።

የአመልካች ቅሬታ በተጠሪ በኩል የተሰጠው ዋስትና እንደ ሌሎች ተራ ዋስትና እንዳልሆነ በቅድመ ሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ ዋስትና በመሆኑ የክፍያ ጥያቄ እንደቀረበ የሚከፈል የባንክ ዋስትና መሆኑን ስር ፍርድ ቤቶች ተቋራጩ የሰራው ስራ ግምትና በግንባታ ቦታ የቀረው ንብረት ግምት በማስገመት ከቅድመ ክፍያ ገንዘብ ውስጥ እንዲቀነስ መወሰኑ ስህተት ነው የሚል ነው። በአመልካች እና ተጠሪ መካከል ያለው ዋስትና ዓይነት በቅድመ ሁኔታ ላይ ያልተመሰረት መሆኑ ግራ ቀኙን አላከራከረም። በቅድመ ሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ ዋስትና ማለት ባንኩ በተጠየቀ ጊዜ የሚከፈል እንደ ቼክ አይነት ዋስትና ነው። በቅድመ ሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ ዋስትና የህንፃው ተቋራጭ የሰራው ስራ በባለሞያ ተገምቶ በግምቱ ልክ ገንዘብ ሊቀነስ ይገባል በማለት ክርክር ለማድረግ ዕድል የሚሰጥ ዋስትና አይደለም። ከባንክና ከኢንሹራንስ የሚሰጡ የዋስትና አይነቶች በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ እና በሁኔታ ላይ የተመሰረተ ተብሎ ይታወቃሉ።

በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የዋስትና ዓይነት በሚሆንበት ጊዜ በውሉ መሰረት ህንፃ ተቋራጭ የውል ግዴታ መፈፀም አለመፈፀም ግምት ውስጥ ሳይገባ የቅድመ ክፍያ ገንዘብ እንዲከፍል በአሰሪው በኩል ጥያቄ በቀረበ ጊዜ ባንኩ የሚከፍለው የዋስትና አይነት ሲሆን በቅድመ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ዋስትና በሚሆንበት ጊዜ በህንፃ ተቋራጩ በኩል የተሰራ ስራ ካለ ግምት ውስጥ ገብቶ በሰራው ስራ መጠን ገንዘቡ ተቀንሶ ያልሰራው ስራ መጠን ብቻ የሚከፈል የዋስትና አይነት ነው።

አሁን በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ የሰጠው ዋስትና አይነት በቅድመ ሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ ዋስትና አይነት በመሆኑ በዋስትና ጊዜ ገደብ ውስጥ በተጠየቀ ጊዜ የዋናው ውል መፈፀም ወይም አለመፈፀም ወይም በከፊል መፈፀሙን ምክንያት በማድረግ ተጠሪ ለመከራከር መብት የሚሰጥ ዋስትና አይነት አይደለም። አመልካች ውሉ አልተፈፀመም ስለዚህ በገባው የዋስትና ግዴታ

መሰረት ክፈለኝ ብሎ በጠየቀ ጊዜ ተጠሪው የዋናውን ውል መፈፀም ወይም አለመፈፀም ማረጋገጥ ሳያስፈልገው ለመጠየቅ መብት የሚሰጥ የዋስትና ግዴታ ሰነድ ነው፡፡ ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን የዋስትና ሰነድ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ለአመልካች ለመክፈል ግዴታ ሊገባ የቻለው በፍላጎት እና በስምምነት ነው፡፡ ውሉ በሁለቱ ተዋዋዮች መካከል በፍ/ብ/ህ አንቀፅ 1731 መሰረት ህግ ስለሆነ ተጠሪ በውሉ መሰረት ይገደዳል፡፡

በአመልካችና በተጠሪ መካከል ያለው ዋስትና በቅድመ ሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ ዋስትና ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤቶች በተክለብርሃን አምባዬ ህንፃ ስራ ተቋራጭ የተሰራው ስራ እና በግንባታ ቦታ የቀሩ ንብረቶች ግምት ከቅድመ ክፍያ ገንዘብ ውስጥ ሊቀነስ ይገባል በማለት የሰጡት ፍርድ የዋስትና አይነት እና የውሉን ሁኔታ ያላገናዘበ ፍርድ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡

ሲጠቃለል በአመልካችና ተጠሪ መካከል ያለው የዋስትና ዓይነት በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ ዋስትና በመሆኑ በቅድመ ሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ ዋስትና ደግሞ በዋስትና ጊዜ ገደብ ውስጥ በተጠየቀ ጊዜ የዋናውን ውል መፈፀም አለመፈፀም ምክንያት በማድረግ ለመከራከር ለተጠሪ መብት የማይሰጥ ዋስትና አይነት ስለሆነ የስር ፍርድ ቤቶች በተቋራጩ የተሰራው ስራ እና በግንባታ ቦታ የቀረው ንብረት ግምት ከቅድመ ክፍያ ገንዘብ ውስጥ ተቀንሶ ቀሪ ገንዘብ ተጠሪ እንዲከፍል መወሰኑ የዋስትና ባህሪይ እና በመካከላቸው ያላቸው ውልን ያላገናዘበ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 168954፣ 191402 እና 235868 መሰረት የሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉምን የሚጣረስ ነው፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጣቸው ውሳኔዎች በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አስገዳጅ እንደሆኑ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 10(2) ስር አስገዳጅ ድንጋጌ ተደንግጎ ስለሚገኝ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ከላይ በተዘረዘረው መሰረት በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 2(4)(ሸ) እና አንቀፅ 10(1)(ለ) መሰረት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 265642 በቀን 07/04/2014 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 219953 በቀን 24/04/2015 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስነ ስርአት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9(1)(ለ) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍርዱ ክፍል ገፅ 5 በውሳኔው ክፍል ተራ ቁጥር 3 ስር ስለወለድ አስመልክቶ የሰጠው ውሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡
3. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡፡
5. በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠ እግድ ካለ ተነስቷል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

**ማስታወሻ፡** - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መዝገብ ቁጥር - 245370

ቀን - 24/04/2017 አ.ም

ዳኞች - ሽመክት አሰፋ

እንዳሻው አዳነ

አለማየሁ ሹናራ

ዋዚሞ ዋሲራ

ዘውዲቱ ታደሰ

አመልካች - ቢትወደድ ጂማ - የቀረበ የለም

ተጠሪዎች - 1. አቶ ሳምሶን መለሰ

2. አቶ ደምሰስ ጌቱ

መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው ለምርመራ ስለሆነ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የተጀመረው በኦሮሚያ ክልል የሴደን ሶዶ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች ከሳሽ ተጠሪዎች ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በተጠሪዎች ላይ ያቀረበው ክስ ይዘት በምስራቅ ታደሰ ዳቢ፣ በምእራብ እና ደቡብ መንገድ በሰሜን ቢትወደድ ጅማ የሚዋሰን ሁለት ቀርጥ እንዲሁም በምስራቅ አረጋሽ ግራኝ በምእራብ ለኤልጀ ባንቲ በሰሜን ታደሰ ዳቢ እና በደቡብ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

መዲና ሰኢድ የሚያዋስኑት ሁለት ቀርጥ በተጨማሪም በምስራቅ እና በሰሜንና በደቡብ መንገድ በምዕራብ በይራባ ወሽንቦ ቀበሌ የሚዋሰን አንድ ቀርጥ በድምሬ አምስት ቀርጥ ይዞታዮን ተከሳሾች ከ 10/10/2013 ኢ.ም ጀምሮ እንዳልጠቀምበት የከለከሉኝ በመሆኑ እንዲለቁልኝ እንዲወሰን የሚል ነው፡፡

ከተከሳሾች በኩል ለክሱ የተሰጠው መልስ የገጠር እርሻ ይዞታ ክርክር በቀጥታ ክስ ፍርድ ቤት ሊቀርብ አይገባም በመጀመሪያ በመሬት አስተዳደር የሚፈታ ጉዳይ ነው፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆነው መሬት የከሳሽ ሳይሆን አያታችን ሟች ወ/ሮ ረጋቱ ገለቴ በ 1969 ኢ.ም እንደ አንድ አርሶ አደር የተሰጣት ነው፡፡ በስሟ ምስክር ወረቀት ያላት ናት አባቶቻችን ከአያቶቻችን ቀድመው ስለሞቱ በውርስ የአያታችንን አግኝተናል፡፡ ከሳሽ ግብር እየገበርኩበት ነው የሚለው መሬት ሌላ መሬት ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን የፅሁፍና ቃል ክርክር ከሰማ በኋላ ተከሳሾች በህገወጥ መንገድ የከሳሽ መሬት ይዘዋል ወይስ አልያዙም? ሁከት አለ ወይስ የለም የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ የግራ ቀኙን የሰው ምስክሮች ቃል ሰምቷል፡፡ ፍርድ ቤቱ ይዞታው የከሳሽ ነው ተከሳሾች ለከሳሽ እንዲለቁ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ተከሳሾች ቅር በመሰኘት ይግባኝ ቅሬታቸውን ለከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ወገኖች ካከራከረ በኋላ የወረዳ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ የማን ነው? በማን ስም ነው የተመዘገበው? ከሳሽ በምን መልኩ አግኝቶ እየተጠቀመበት ነው? ለምን ያህል ጊዜ እየተጠቀመ ነው የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ የሴደን ሶዶ ወረዳ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም እና የአከባቢ አዋቂ ሽማግሌዎች እንዲጣራ በማድረግ በማስረጃ አጣርቶ እንዲወስን ሲል በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ አንቀፅ 343(1) መሰረት ሽሮ መልሶታል፡፡ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሽሮ ከተመለሰ በኋላ ወረዳ ፍርድ ቤት የወረዳው ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ፅ/ቤት ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ የማን እንደሆነ አጣርተው እንዲያሳውቁ ትዕዛዝ በመስጠት በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ተጣርቶ የቀረበው ማስረጃ ለክርክሩ መነሻ የሆነው መሬት ከጅምሩ የቡልቱሜ ታለገኝ እና የረጋቱ ገለቴ በክፍፍል ያገኙት መሆናቸውን ከሳሽ ለተከሳሾች አያት ረጋቱ ገለቴ አርሶ ሲያካፍል ቆይቶ የተከሳሾች አያት ከሞተች ጊዜ እስከ 2013 ኢ.ም ድረስ በእጅ ይዞ እየተጠቀመበት መሆኑን በ 2013 ኢ.ም ብቻ ተከሳሾች ይህንን ይዞታ የያዙ መሆናቸውን በ 2014 ኢ.ም ይህ ይዞታ ግራ ቀኙ ሲከራከሩ ስለነበር በማንም ስም ሳይያዝ የታለፈ መሆኑን አረጋግጧል፡፡

የስር ፍርድ ቤት ከከፍተኛ ፍርድ ቤት በተመለሰው ጭብጥ መሰረት ከወረዳ ገጠር መሬት አስተዳደር መግለጫ እንዲቀርብ ካደረገ በኋላ ይዞታው ከመነሻው የተከሳሾች አያት መሬት መሆኑን

ይዞታው በከሳሽም ሆነ በተከሳሽ ስም ያልተመዘገበ መሆኑን ለሁለቱም ወገኖች ማስረጃ የሌላቸው መሆኑን ይዞታውን ከሳሽ ያገኙበት መንገድ ለተከሳሾች አያት ሲያርስ የነበረ መሆኑን እንጂ በምን መልኩ እንዳገኘ የማይገልፅ ቢሆንም ከረጅም አመት ጀምሮ ከሳሽ ሲጠቀም የነበሩ መሆኑን የከሳሾች ምስክሮች እና የወረዳው ገጠር መሬት አስተዳደር ያስረዳ በመሆኑ በሶስት ቦታ የሚገኙ መሬቶችን ተከሳሾች ለከሳሽ እንዲለቁ ሲል ወስኗል፡፡

ተከሳሾች በወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘታቸው ይግባኝ ቅሬታቸውን ለደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ቅሬታ በአጭሩ ከሳሽ አያታችን በህይወት በነበረችበት ጊዜ ለአያታችን የሚያርስ እንጂ ለከሳሽ የተሰጠ ይዞታ ማረጋገጫ ሳይኖር የአያታችን ይዞታ ለከሳሽ እንዲለቅ የተወሰነው ስህተት ነው፡፡ ይዞታው የአያታችን መሆኑ ከወረዳው ገጠር መሬት አስተዳደር ተረጋግጧል፡፡ ከሳሽ ይዞታውን ከመንግስት ተመርቶ ስለማግኘቱ ወይም በውርስ ወይም በስጦታ ስለማግኘቱ ምንም አይነት ማስረጃ ሳያቀርብ ለአያታችን ሲያርስ የቆየውን ከረጅም አመት ጀምሮ ይዟል ተብሎ የአያታችንን ይዞታ እንድንለቅ መወሰኑ ስህተት ነው የሚል ነው፡፡

ይግባኝ ሰሚ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን ሲያከራክር ቆይቶ በመዝገብ ቁጥር 63077 በቀን 12/04/2015 አ.ም በዋለው ችሎት አከራካሪው ይዞታ የተከሳሾች ይዞታ መሆኑን ከሳሽ ለአያታቸው ሲያርሱ የነበረ መሆኑን አያታቸው ከሞተች በኃላ ከ 13 አመት በላይ ሲጠቀምበት የቆየ መሆኑን በ 2013 አ.ም ይህን ይዞታ ተከሳሽ በሽምግልና ከከሳሽ እጅ መውሰዳቸውንና በኃይል አለመያዛቸው በሰው ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ይዞታው የተከሳሾች አያት ይዞታ ስለመሆኑ ከወረዳው ገጠር መሬት አስተዳደር ተረጋግጧል፡፡ ይዞታው በከሳሽ ሆነ በተከሳሾች ስም ያልተመዘገበ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ከሳሽ ይዞታውን በምን መልክ እንዳገኙ በማስረጃ አልተረጋገጠም ከመዝገቡ ውስጥ የተረጋገጠው እውነታ ይዞታው የተከሳሾች አያት ይዞታ ከሳሽ አርሶ በጋራ ሲጠቀም የቆየ መሆኑን ተከሳሾች የያዙበት ሁኔታ የአያታችን ይዞታ ነው በማለት ከሳሽ እንዲሰጥ በሽምግልና ጠይቋቸው ከሳሽ የለቀቀላቸው መሆኑ በሰው ምስክሮች ተረጋግጧል፡፡

የገጠር መሬት አዋጅ መሰረት የአርሶ አደር ይዞታ የቤተሰብ አባል ያልሆነ ሰው በስጦታም ሆነ በውርስ ለማግኘት መብት የሌለው መሆኑን ከሳሽ ይዞታውን ያገኙበት መንገድ ያልታወቀ እና የይዞታ ምስክር ወረቀት የሌለው መሆኑን ይዞታው የተከሳሾች አያት ይዞታ ሲሆን ከሳሽ ለአያታቸው እያረሱ በጋራ ሲጠቀሙ እንደነበር የተረጋገጠ በመሆኑ ለረጅም አመት ይዞታውን በመያዝ ብቻ የይዞታ ባለመብት ሊያደርገው ስለማይችል ከሳሽ የመክሰስ መብትና ጥቅም የለውም በማለት የስር ወረዳ ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሮታል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ቅሬታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ፍርድ ቤቱም ቅሬታውን ባለመቀበል መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ አመልካች በመቀጠል ሰበር ቅሬታ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ሰበር ችሎቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትንና የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ አፅንቶታል፡፡

የአሁን ሰበር ቅሬታ የቀረበው ይህን የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጀምሮ እስከ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰጡት ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች ሰበር ቅሬታ ይዘቱ በአጭሩ በእጅ አድርጎ ሲጠቀምበት የቆየ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ይዞታውን ለተጠሪዎች እንደለቅ መወሰናቸው ስህተት ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በቅፅ 13 በመዝገብ ቁጥር 69302 ላይ የሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉምን የሚጣረስ ነው፡፡ ክሱ በ 10 አመት ይርጋ ቀሪ ነው፡፡ ተጠሪዎች ይዞታውን በ 2013 ኢ.ም የያዙት በስምምነት ነው የተባለው በማስረጃ ያልተረጋገጠ ነው፡፡ የክልሉ ሰበር የመፋለም ክስ ነው የሁከት ክስ አይደለም ያለበት ሁኔታ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ እንዲሻርልኝ የሚል ነው፡፡

ይህ ሰበር ችሎት አመልካች ከ 13 አመት በላይ ለሆነ ጊዜ ይዞታውን ይዞ ሲገለገል ቆይቶ ተጠሪዎች በኃይል በመያዛቸውና እንዳይጠቀሙ በመከላከላቸው እንዲለቁለት ዳኝነት በጠየቀበት ሁኔታ አመልካች በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ አንቀፅ 33 መሰረት ክስ ለማቅረብ የሚያስችለው መብትና ጥቅም የለውም ያቀረበው የዳኝነት ጥያቄ የመፋለም እንጂ የሁከት ይወገድልኝ ክስ ባለመሆኑ ይዞታዎቹን በውርስ በስጦታ ወይም በምሪት ማግኘቱን አላስረዳም በሚል የተጠሪዎች የኃይል ተግባር በሚያበረታታ መልኩ ይዞታዎቹን ሊለቁ አይገባም ተብሎ በስር ይግባኝ ሰሚ ችሎቶችና ሰበር ሰሚ ችሎት መወሰኑ አግባብነት ከመሰረታዊ የማስረጃ ምዘና መርህ አንፃር ከፍ/ብ/ስ/ስ/ህ አንቀፅ 33፣ 182 እና ከሰበር መዝገብ ቁጥር 37761 አንፃር ለማጣራት ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪዎች የበኩላቸውን መልስ በ 03/12/2016 ኢ.ም በ 04 ገፅ አቅርበው ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

ይዘቱ በአጭሩ ለክርክሩ መነሻ የሆነው መሬት የአያታችን መሬት መሆኑንና አመልካች መሬቱን በሽምግልና በፍላጎት የሰጠን መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ የይርጋ ክርክር አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያላነሳውን አዲስ ክርክር ማቅረቡ ስህተት ነው፡፡ የአመልካች ዳኝነት ጥያቄ ሁከት ይወገድልኝ ክስ ሳይሆን የመፋለም ክስ ነው፡፡ መሬቱ የአመልካች ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 130/99 አንቀፅ 5(5) እና ደንብ ቁጥር 151/2005 አንቀፅ 3 መሰረት ይዞታውን እንዴት እንዳገኘ ማስረዳት ያለበት ሲሆን አላስረዳም፡፡ ይዞታዎቹ የተጠሪዎች አያት እንደሆነና በወቅቱ ተጠሪዎች አቅመ አዳም ስላልደረስን አሁን እድሜያችን ለአቅመ አዳም ሲደርስ በአከባቢ ሽምግሌ አመልካች መሬቱን እንዲለቅልን ጠይቀን አመልካች ተስማምተው እንዲለቀቅልን በሰው ማስረጃና የወረዳው መሬት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

አስተዳደር አረጋግጧል፡፡ የአያታችን መሬት አመልካች እንዲለቁልን በሽምግልና ጠይቀን በስምምነት ከሰጠ በኃላ በኃይል እንደያዘን ለማስመሰል ያቀረበው ክስ መሆኑ ተረጋግጦ በስር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ፍርድ በአግባቡ ስለሆነ እንዲያፀናልን የሚል ነው፡፡ አመልካች በ 17/12/2016 ዓ.ም በ 04 ገፅ የመልስ መልሱን ሰበር ቅሬታ በማጠናከር አቅርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ በተገለፀው መሰረት በመጠቃለሉ እኛም ለሰበር ቅሬታ መነሻ የሆነውን ፍርድ፣ በግራ ቀኙ በኩል የቀረበውን ክርክር ይህ ችሎት ካስቀረበው ጭብጥ መነሻ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ ተጠሪዎች የያዙት በሽምግልና የአያታቸውን መሬት አመልካች በስምምነት ሰጥቷል እንጂ በጉልበት አልያዘም በማለት አመልካች ክሱን ለማቅረብ መብትና ጥቅም የለውም ተብሎ ውድቅ የተደረገበት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ አንቀፅ 33፣ 182 እና ከሰበር መዝገብ ቁጥር 37761 አንፃር አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

መርምረን እንደተረዳነው ከሆነ የአመልካች ክስ ተጠሪዎች 5 ቀርጥ መሬቴን ከሰኔ 2013 ዓ.ም ጀምሮ እንዳልጠቀም በጉልበት ይዘው የከለከሉኝ ስለሆነ እንዲለቁልኝ የሚል ሲሆን ተጠሪዎች ይዞታው የአያታቸው መሆኑን ከረጅም አመት ጀምሮ በአያታቸው ረጋቱ ገለቴ ስም ተይዞ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያለው መሆኑን ከአያታቸው በውርስ ያገኙ መሆኑን በመጥቀስ ክደው ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ይዞታ የማን እንደሆነ አረጋግጦ የወረዳው ገጠር መሬት አስተዳደር መግለጫ እንዲሰጥ በጠየቀው መሰረት የወረዳው ገጠር መሬት አስተዳደር ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ የተጠሪዎች አያት ወ/ሮ የረጋቱ ገለቴ እና የቡልቴሜ ታለገኝ መሆኑን አመልካች ለተጠሪዎች አያት ረጋቱ ገለቴ አርሶ ምርቱን እኩል ሲያካፍል ቆይቶ የተጠሪዎች አያት ከሞቱ በኃላ እስከ 2013 ዓ.ም ድረስ በእጅ ይዞ እንደቆየ አረጋግጧል፡፡ አንድ አርሶ አደር የገጠር እርሻ መሬት የሚያገኝበት መንገድ ከመንግስት በምሪት ወይም በስጦታ ወይም በውርስ ነው፡፡ ከእነዚህ ከሶስቱ መንገዶች ውጪ የገጠር እርሻ መሬት ሊያገኝ አይችልም፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይ አመልካች መሬቱን የያዘበት መንገድ ለተጠሪዎች አያታቸው እኩል ለማረስ እንደያዘ የይዞታ ባለቤት የተጠሪዎች አያታቸው መሆኑን በገለልተኛ አካል ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ይዞታውን ከላይ በተገለፀው ከሶስት መንገዶች በአንደኛው መንገድ ስለማግኘቱ አላስረዳም፡፡ አመልካች ለረጅም አመት ይዞታውን የያዙበት መንገድ የተጠሪዎች አያታቸውን አርሶ ምርቱን እኩል አካፍሎ እንዲሰጥተብሎ ነው እንጂ ለረጅም አመት ከህጋዊ አካል ተመርቶ ስለመያዙ አልተረጋገጠም፡፡ አመልካች የይዞታ ባለቤት ሊያደርግ የሚችል አንድም ማስረጃ ሳይኖር

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

ለረጅም አመት በእጁ በመያዙ ብቻ የይዞታ ባለቤት ሊያደርገው አይችልም፡፡ ለረጅም አመት የያዘውም የይዞታ ባለቤት ጠፍቶ ሳይሆን ለይዞታ ባለቤቱ እኩል ምርቱን አካፍሎ ለመስጠት በስምምነት የያዘ በመሆኑ ተጠሪዎች ይዞታውን እንዲለቅ በጠየቁ ጊዜ ከመልቀቅ ውጪ ሌላ የባለቤትነት ጥያቄ ሊያነሳ አይችልም፡፡

በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንደተረጋገጠው ከ 2013 አ.ም በኃላ ተጠሪዎች ይዞታውን የያዙት ከአመልካቾች ጋር በሽምግልና ተጠይቀው አመልካች በፍቃዱ ከመስጠት ውጪ በጉልበት እንዳልያዘ በስር ፍርድ ቤት በማስረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ በመሆኑ ተጠሪዎች ይዞታውን ከአመልካች እጅ ቀምተው በጉልበት ስለመያዛቸው ከአመልካች በኩል የተረጋገጠ ነገረው የለም፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ የአመልካች ስለመሆኑ ማስረጃ የመመዘንና የመመርመር ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ያልተረጋገጠ በመሆኑ ከክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጀምሮ እስከ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ የተሰጠ ፍርድ የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ይዞታ ለረጅም አመት አመልካች ሊይዝ የቻለው ከመንግስት በህጋዊ መንገድ ተመርቶ ወይም በስጦታ ወይም በውርስ ሳይሆን የተጠሪ አያታቸው በጋራ እንዲያርስ በመስጠታቸው ምክንያት በመሆኑ የይዞታው ባለቤት የተጠሪዎች አያት ናቸው እንጂ አመልካች ስላልሆነ አመልካች ለረጃም ዓመት በጋራ ለማረስ የአላባ ጥቅም ለማግኘት መያዙ የይዞታ ባለቤት ሊያደርገው ስለማይችል የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጀምሮ እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ የተሰጠው ፍርድ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት በመሆኑ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የኦሮሚያ ክልል የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 63077 በቀን 12/04/2015 አ.ም የሰጠው ውሳኔ፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 411747 በቀን 17/05/2015 አ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 421427 በቀን 28/06/2015 አ.ም የሰጠው ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያልተፈፀመ በመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስነ ስርአት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9(1)(ሀ) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. በዚህ ችሎት የተሰጠ እግድ ካለ ተነስቷል፡፡

<u>ማስታወሻ</u>፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

## ትዕዛዝ

- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

**የሰ/መ/ቁ 246386**

ታህሳስ 23ቀን 2017ዓ/ም

ዳኞች፡-ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ብርቅነሽ እሱባለው

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካቾች፡ - 1.ወ/ሮ ፋንቱ ዘነበ

2.ጉብታ የገበያ ማዕከል አክሲዮን ማህበር ጠበቃ ግርማ ፈይሳ ቀረቡ

ተጠሪ፡- በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የእንጦጦ ስብሐት ቅድስት ስላሴ ቤተ-ክርስቲያን - ጠበቃ ደረጀ ሙሉጌታ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ የቀረበው አመልካቾች የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 226382 መጋቢት 29 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በቀን 02/03/2013 ዓ.ም የሰጠውን ብይን በማጽናቱ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በቀን 27/07/2014 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም በ30/08/2015 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡

**ማስታወሻ፡** - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ሲታይ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ በመሆን አመልካቾች 1ኛ እና 4ኛ ተከሳሽ በመሆን እንዲሁም በዚህ ክርክር ተካፋይ ያልሆኑት እነ ሳልሳይ ኤፍሬም ጌታቸው 4 ሰዎች በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት 2ኛ፣ 3ኛ፣ 5ኛ እና 6ኛ ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረበችው የተሻሻለ ክስ የአባ ኃይለስላሴ መገኖ ርስት እና ንብረት የሆነው አንድ ጋሻ ይዞታ ሰኔ 17 ቀን 1948 ዓ.ም በተደረገ ግልጽ ኑዛዜ የተሰጣት መሆኑን ኑዛዜው በከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 169/55 ግንቦት 13 ቀን 1955 ዓ.ም መጽደቁን እና ከሳሽ ይዞታውን ተረክባ ስታስተዳድር የቆየች መሆኑን፤ ከአንድ ጋሻ መሬት ላይ 1192 ካ.ሜ ይዞታ ቀንሳ ለአገልጋይ ካህናት ደመወዝ መክፈያ ይሆን ዘንድ የ1ኛ አመልካች ባለቤት ለነበሩት ለአቶ ኤፍሬም ጌታነህ በወር ብር 30 (ሰላሳ) ሂሳብ ለአምስት ዓመታት አከራይታ የኪራይ ውሉ እስከ 1967 ዓ.ም እየተራዘመ መቆየቱን፤ ይዞታው ያልተወረሰ እና የግል ቤቴ ነው በማለት አቶ ኤፍሬም ጌታነህ በ2004 ዓ.ም ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ እንደ ቅደም ተከተላቸው የስር 5ኛ እና 6ኛ ተከሳሾች የነበሩት ጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 01 አስተዳደር እና ጉለሌ ክ/ከተማ መሬት አስተዳደር የቤት ቁጥር 815(ለ) በሚል በአቶ ኤፍሬም ጌታነህ ስም ተመዝግቦ ስም እንዲዞር ማድረጋቸውን፤ ይህንኑ ይዞታ የአቶ ኤፍሬም ጌታነህ ወኪልና የስር 4ኛ ተከሳሽ(2ኛ አመልካች) የቦርድ ሰብሳቢ በሆኑት አቶ መኮንን አያሌው እና የተጠሪ ፀሀፊ ዲያቆን ተስፋሚካኤል ታደሰ አመልካችነት ይዞታው ወደ አቶ ኤፍሬም ጌታነህ እንዲተላለፍ በመጠየቁ ህዳር 17 ቀን 2005ዓ.ም ቁጥሩ 22/69/28322/00 የሆነ ካርታ በአቶ ኤፍሬም ጌታነህ ስም ተዘጋጅቶ ተሰጥቷል፡፡ ነሐሴ 15 ቀን 2005 ዓ.ም በተደረገ በሽያጭ ውል ለ2ኛ አመልካች(ስር 4ኛ ተከሳሽ) ተላልፏል፡፡ የተጠሪ ይዞታ ከህግ ውጪ የተላለፈ በመሆኑ የስር 5ኛ እና 6ኛ ተከሳሾች የይዞታውን ባለቤት በአግባቡ ሳያጣሩ በአቶ ኤፍሬም ጌታነህ ስም በ17/3/2005ዓ.ም አዘጋጅተው የሰጡትን ካርታ እንዲሰርዙ፤ በሟች አቶ ኤፍሬም ጌታነህ እና በስር 4ኛ ተከሳሽ(2ኛ አመልካች) መካከል የተደረገው በ15/12/2005ዓ.ም የተደረገው ውል እንዲሰረዝ፤ የስር 5ኛ ተከሳሽ አለአግባብ በሰጠው መረጃ መሰረት ለስር 4ኛ ተከሳሽ(2ኛ አመልካች) የተሰጠው ካርታ እንዲሰረዝ፤ በምትኩ የስር 5ኛ እና 6ኛ ተከሳሾች ለይዞታው ለተጠሪ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንዲሰጡ፤ በይዞታው ላይ ያለን ንብረት 2ኛ አመልካች አንስቶ ይዞታውን ለተጠሪ እንዲያስረክብ እንዲወሰን በማለት ዳኝነት ጠይቃለች፡፡ ማስረጃዎችንም አያይዛለች፡፡

አመልካቾችን ጨምሮ የስር ተከሳሾች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን አቅርበው ፍርድቤቱ መቃወሚያዎቹን መርምሮ በ2/10/2013ዓ.ም በዋለው ችሎት በብይን ውድቅ አድርጓቸዋል፡፡

1ኛ አመልካች ለፍሬ ነገሩ ባቀረቡት መልስ እኔና ባለቤቴ በይዞታችን ላይ በአቶ ኤፍሬም ጌታነህ ስም የንግድ ስራ ፈቃድ አውጥተን የመንግስት ግብርም እየከፈልን ለብዙ አመታት ስንገለገልበት ቆይተን ከግዜ በኋላ ንብረታችን ስለሆነ ሸጠናል እንጂ የቤተክርስትያኒቱን ይዞታ አልነካንም፤ በአባ ኃይለስላሴ መገኖ በ17/10/1948ዓ.ም ተደረገ የተባለውም ሆነ በፍርድ ቤት ውሳኔ ጸድቋል የተባለው ኑዛዜም አልተደረገም፤

በንብረታችንም ላይ ሊደረግ አይገባም፤ በቤተክርስቲያኒቱ ይዞታ ስር ይገኛል የሚባለው ቦታ የቤት ቁጥር 0000 እንጂ የቤት ቁጥር 815(ለ) አይደለም፡፡ ተጠሪ በ1953ዓ.ም የዘይት መጭመቂያ ሰርታ አላከራየችንም፤ የኪራይ ውልም የለንም፡፡ ለክሱ መነሻ የሆነው ይዞታ የከተማ ቦታንና ትርፍ ቤትን የመንግስት ለማድረግ የወጣ አዋጅ ቁጥር 47/67 በፊት ጀምሮ በይዞታችን ስር ሆኖ ስንተዳደርበት የነበረ ይዞታ ሲሆን አዋጁ ሲወጣ በይዞታችን ስር በመሆኑ አልተወረስንም፤ በአዋጁ ባልተወረሰው ቦታ ላይ ከሚመለከተው አካል የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የወሰድን በመሆኑ በህጋዊ መንገድ ተጣርቶ የተሰጠን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ሊሰረዝ አይገባም፡፡ የኪራይ ገቢ ደረሰኝ ተብለው የቀረቡት ማስረጃዎች ከ1ኛ አመልካች ወይም ከአቶ ኤፍሬም ጌታነህ የሚሉ ባለመሆናቸው ተቀባይነት የላቸውም፡፡ ስለሆነም ክሱ ውድቅ እንዲደረግ በማለት ተከራክረዋል፡፡ ማስረጃዎችንም አቅርበዋል፡፡

አሁን በሰበር ክርክሩ ላይ የሌሉት የስር 2ኛ፤ 3ኛ ተከሳሾች ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚሉበትን ምክንያት በመዘርዘር ያቀረቡ ሲሆን፤ የስር 5ኛ እና 6ኛ ተከሳሾችም ባቀረቡት መልስ ለክርክሩ መነሻ የሆነው የቤት ቁጥሩ 815(ለ) የሆነው ቤትና ይዞታ አቶ ኤፍሬም ጌታነህ በ19/6/1955ዓ.ም ከአባ ኃይለስላሴ መገኖ በሽያጭ ያገኙት መሆኑን በማረጋገጥ ካርታ መሰጠቱ አግባብ ነው፡፡ የአቶ ኤፍሬም ጌታነህ ወኪል የሆኑት አቶ መኮንን አያሌውም ህጋዊ ውክልና ይዘው የአቶ ኤፍሬም ጌታነህ የግል ንብረት የሆነውን የንግድ ቤታቸውን ህጋዊ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ማውጣታቸው በህግ አግባብ ነው፡፡ ለይዞታው የተሰጡት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታዎች በአግባቡ ተጣርተው የተሰጡ በመሆናቸው የሚሰረዙበት ምክንያት ባለመኖሩ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ በማለት ተከራክረዋል፡፡ ማስረጃዎችንም አቅርበዋል፡፡

2ኛ አመልካች(ስር 4ኛ ተከሳሽ) ባቀረበው መልስ ተጠሪ በስሟ የጸደቀ ኑዛዜ የለም፤ የቀረበውም ኑዛዜ ህጋዊ አይደለም፡፡ ጉለሌ ክ/ከተማ እና የወረዳ 1 አስተዳደርም ለቤተክርስትያኑ ይዞታ የሰጠው ማረጋገጫ የለም፤ ተጠሪ በወረዳ 1 የቤት ቁጥር 815(ለ) ቤት ውስጥ የሰራችው የዘይት መጭመቂያም የለም፤ ማስረጃም አልቀረበም፡፡ አቶ ኤፍሬም ጌታነህ ለመከራየታቸው የቀረበ ማስረጃ የለም፡፡ ከአቶ ኤፍሬም ጌታነህ ጋር ተስማምተን በ15/12/05ዓ.ም የቤት ሽያጭ ውል የተዋዋልን በመሆኑ ይህንኑ ተከትሎ የተሰጠው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ሊሰረዝ አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡ ማስረጃዎችንም አቅርቧል፡፡

ፍርድቤቱም ክሱን ሰምቶ፤ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት ትእዛዝ ከሰጠ እና የግራቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኋላ ከሰነድ ማስረጃዎች ጋር እንዲሁም ለሰጠው ትእዛዝ ከቀረበለት ምላሽ ጋር ጉዳዩን መርምሮ ክርክር የተነሳበትን ይዞታ ሟች አባ ሃይለስላሴ መገኖ ለተጠሪ በኑዛዜ ሰጥተው ለተጠሪ የተላለፈው ይዞታ ውስጥ ያለውን የዘይት መጭመቂያ ንግድ ሟች አቶ ኤፍሬም ተከራይተው ሲገለገሉ ከቆዩ በኋላ ይህ ይዞታ ሟች አቶ ኤፍሬም ጌታነህ በሽያጭ ውል የተገኘ በማስመሰል ለስር 5ኛ እና 6ኛ ተከሳሾች አቅርበው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የወሰዱበት ይዞታ የተጠሪ ነው በማለት ወስኗል፡፡ አቶ ኤፍሬም ጌታነህ በይዞታው ላይ ካርታ የወሰዱት በ19/6/1955ዓ.ም ተደርጓል የተባለን የሽያጭ ውል በማቅረብ ሲሆን ይህ ውል ደግሞ

ያልተደረገ እና በሀሰት የተዘጋጀ በመሆኑ በይዞታው ላይ ለሚች አቶ ኤፍሬም ጌታነህ ተሰጥቶ የነበረው የባለይዞታነት ሰነድ ሊሰረዝ ይገባል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ሚች አቶ ኤፍሬም ጌታነህ ይዞታውን ለ2ኛ አመልካች(ስር 4ኛ ተከሳሽ) በሽያጭ ያስተላለፉት በይዞታው ላይ መብት ሳይኖራቸው በመሆኑ በሚች አቶ ኤፍሬም ጌታነህ እና በ2ኛ አመልካች መካከል በ15/12/05ዓ.ም የተደረገው የሽያጭ ውል ህገወጥ በመሆኑ ውሉ ሊሰረዝ ይገባል፡፡ ለ2ኛ አመልካችም በይዞታው ላይ የተሰጠው ካርታ በስር 5ኛ እና 6ኛ ተከሳሾች እንዲሰረዝ እና በምትኩ በይዞታው ላይ ለተጠሪ አዲስ የባለቤትነት ካርታ እንዲሰጥ በማለት ወስኗል፡፡ ተጠሪ 2ኛ አመልካች ግንባታውን አንስቶ ይልቀቅ በማለት ያቀረበችውን ጥያቄ በተመለከተ ህንጻው የሀገር ሀብት በመሆኑ፤ በህንጻው የሚገለገሉት ዜጎች ከመኖራቸው አንጻር ፍትሃዊ ስለማይሆን በስምምነት በሚያቀርቡት ግምት፤ መስማማት ካልቻሉ በገለልተኛ ባለሙያ በሚቀርብ የገበያ ግምት መሰረት ተጠሪ ግምቱን ከፍላ ህንጻውን እንድታስቀር፤ ተጠሪ ግምቱን ከፍላ ማስቀረት ያልቻለች ወይም ያልፈለገች እንደሆነ 2ኛ አመልካች ግምቱን በመክፈል እንዲያስቀረው በማለት ወስኗል፡፡

የፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት በሰጠው ብይን እና ውሳኔ አመልካቾች ይግባኝ፤ ተጠሪ ደግሞ በፍሬጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ በከፊል ቅር በመሰኘት መስቀለኛ ይግባኝ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም መልስ ከተቀበለ በኂላ ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍርድቤት በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ላይ የሰጠውን ብይን በማጽናት ወስኖ፤ በፍሬጉዳዩ የቀረበውን ክርክር መርምሮ የስር ፍርድቤት ተጠሪ የግንባታውን ግምት መክፈል ካልቻለች ወይም ካልፈለገች ግምቱን 2ኛ አመልካች(የስር 4ኛ ተከሳሽ) ለተጠሪ ከፍሎ እንዲያስቀረው በማለት የሰጠውን የውሳኔ ክፍል በመሻር፤ ቀሪውን የስር ፍርድቤት የውሳኔ ክፍል በማጽናት ወስኗል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታም የቀረበውም ከላይ በተገለጸው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን አጭር ይዘቱም፡- ተጠሪ በ1948 ዓ.ም ተደርጎልኛል ያለችው ኑዛዜ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ገፆች ላይ ያልተፈረመበት ተራ ሰነድ ነው የሚል መከራከሪያ አቅርበን እንዲሁም የኪራይ ውል አባ ኃ/ሥላሴ ራሳቸው በ1953 ዓ.ም አከራይተው እያለ ያቀረብነውን መከራከሪያ በማለፍ ፍ/ቤቶቹ የሰጡት ውሳኔ ተገቢነት የለውም፡፡

ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የቤተክርስቲያኗ ዐቃቢት ኑዛዜውን በፌ/ከ/ፍ/ቤት በ1955 ዓ.ም አጸድቀዋል ያለውን በተመለከተ በ1955 ዓ.ም የፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት የለም፤ ጸደቀ የተባለውን ኑዛዜ ወ/ሮ ሙሉነሽ የራሳቸውን የወራሽነት ውሳኔ ያስወሰኑበት እንጂ ተጠሪን ወክለው ያስወሰኑት ውሳኔ የሌለ በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 130284 ቅጽ 22 ላይ የሰጠውን አስገዳጅ ውሳኔ በመቃረን መሰረታዊ የማስረጃ ምዘና ሕግና በመጣስ የሰጡት ውሳኔ ይታረምልን፡፡

ተጠሪ በኑዛዜ አገኘሁ ስትል ለፍ/ቤቱም ያቀረበችው ኑዛዜ በሕግ አግባብ ተቀባይነት የለውም፤ አለው እንኳን ቢባል በኑዛዜ የተገኘን ንብረት በፍ/ብ/ሕ/ቁ 896 ድንጋጌ እና በሰ/መ/ቁ 53729 በተሰጠ ውሳኔ

መሰረት በ10 አመት ጊዜ ካልጠየቀ በይርጋ ይታገዳል በሚል ያቀረብነውን ክርክር በማለፍ ተጠሪ የቤቱ ሕጋዊ ባለቤት መሆኗን የሚያስረዳ ማስረጃ ሳይኖር ከ60 አመት በላይ በ1ኛ አመልካች ባለቤት እና በ1ኛ አመልካች እጅ የነበረን ቤት የተጠሪ ነው በሚል የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ስህተት ነው፡፡

የ1ኛ አመልካች ባለቤት አቶ ኤፍሬም የክርክሩ መነሻ በሆነው ቤት ከ1953 ዓ.ም ጀምሮ ይዘውት ግብሩን ከ1968 ዓ.ም ጀምሮ ለ15 አመት የገበሩ በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1168 እና በሰ.መ.ቁ 89148 በተሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ መሰረት የንብረቱ ባለቤት ሆነው ሳለ የስር ፍርድቤቶች በዚህ ረገድ ያቀረብነውን ክርክር በማለፍ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲታረም፡፡

2ኛ አመልካች በ2005 ዓ./ም ቤቱን ገዝቶ በዚያው ጊዜ የግንባታ ፈቃድ በማውጣት የነበረውን አሮጌ ቤት እና በባዶ ይዞታ ላይ G+5 የሆነ ህንፃ ከ2005 ዓ.ም እስከ 2013 ዓ.ም ህንፃው ሲገነባ ተጠሪ የራሷን ካርታ በራሷ ይዞታ ላይ እያወጣች በነበረችበት ጊዜ አንድም ቀን ይዞታዬ ነው በማለት ሳትቃወም ህንፃው ሊጠናቀቅ ትንሽ ሲቀረው ክስ ያቀረበች ስለሆነ በአንድ ይዞታ ላይ ህንፃ የሰራው ግለሰብ የሰበር ችሎቱ በቅጽ 6 በሰ/መ/ቁ 30101፣ ቅጽ 10 ሰ/መ/ቁ 36638 እና ቅጽ 20 ሰ/መ/ቁ 105125 ህንጻውን እንዲለቅ እንደማይገደድ የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 40/3 እና 40(7) ድንጋጌን በመተርጎም አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሰጠባቸውን ውሳኔዎች በመተላለፍ ፍ/ቤቶቹ ቤቱ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ እንዲታረምልን፤ ወጪና ኪሳራ እንዲከፈለን እንዲወሰንልን የሚል ነው፡፡

ይህ ችሎትም የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ እና የሰበር አጣሪ ችሎቱ ጉዳዩን የመራበትን ትዕዛዝ መርምሮ ለክርክር መነሻ የሆነው ይዞታ 1ኛ አመልካች እና ባለቤታቸው ከ1967 ዓ.ም በፊት ጀምሮ በእጃቸው አድርገው ሲገለገሉበት የነበረና በኃላ በሟች አቶ ኤፍሬም ጌታነህ ስም የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ተሰጥቷቸው እያለ እና 2ኛ አመልካች ደግሞ በሽያጭ ውል ይዞታውንና ቤቱን ገዝቶ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ተሰጥቷቸው እያለ ይዞታው የተጠሪ ነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እና የሽያጭ ውል ተሰርዞ 2ኛ አመልካች ይዞታውን ለተጠሪ እንዲያስረክብ በይዞታው ላይ ላለው ሕንፃ ተጠሪ ለ2ኛ አመልካች ግምት እንዲከፍል በማለት የመወሰኑን አግባብነት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 28(3) መሰረት ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት በ28/11/2015ዓ.ም በተሰጠው ትእዛዝ መሰረት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በ23/12/2015ዓ.ም በተጻፈ ባቀረበችው መልስ 1ኛ አመልካች ከ1967ዓ.ም በፊትም ሆነ ከ1967ዓ.ም ወዲህ የክርክር መነሻ የሆነውን ንብረት ሲገለገሉበት የነበረው በተከራይነት እንጂ በቤት ባለቤትነት መብት እንዳልሆነ በስር ፍርድቤቶች በማስረጃ የተረጋገጠ ነው፡፡ ከካርታ ዝግጅት ጋር በተያያዘ የቀረበውን ነጥብ በተመለከተ አመልካቾች ሻጭ እና ገዥ በመሆን ከመነሻው ጀምሮ በሀሰት የተዘጋጀን ሰነድ በመገልገል በፈጸሙት ተግባር የተገኘ ካርታ ስለመሆኑ የስር ፍርድቤቶች በማስረጃ አጣርተው የሰጡት ውሳኔ አግባብ

ነው፡፡ በዚህ ችሎት ያስቀርባል ከተባለው ነጥብ ውጪ አመልካቾች በሰበር አቤቱታቸው የጠቀሳቸው የማስረጃ እና የፍሬጉዳይ ክርክሮች በመሆናቸው በዚህ የሰበር ችሎት ሊቀርቡ አይገባቸውም፡፡ ስለሆነም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ እንዲጸና፤ ወጪና ኪሳራ እንዲከፈለን እንዲወሰንልን በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾች በ7/1/2015ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታውን አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ፤ ለሰበር ችሎቱ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ እንዲሁም ከተገቢዎቹ የህግ ድንጋጌዎች አንጻር የስር ፍርድቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገመንግስት አንቀጽ 80(3)(ሀ) ሆነ በፌደራል ፍርድቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 እንደተደነገገው ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ስልጣን መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበትን የመጨረሻ ውሳኔ እንዲያርም ነው፡፡ አንድ ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻለው በፌደራል ፍርድቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4) ከ "ሀ-ሸ " ከተዘረዘሩት ውስጥ ቢያንስ አንዱን የሚያሟላ ሆኖ በውጤቱም ፍትሕን የሚያዛባ ጉልህ የህግ ስህተት የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 2(4) ድንጋጌ ይዘት የሚያስገነዝብ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ ፍሬነገርን በማስረጃ የማጣራት በህግ ስልጣን የተሰጠው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት የተጠሪን፤ አመልካቾችን ጨምሮ የሌሎች የስር ተከሳሾችን ማስረጃዎች እንዲሁም ለሚመለከታቸው አካላት ለሰጠው ትእዛዝ የቀረቡለትን ምላሾች ጭምር በመመርመር እና በመመዘን ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ይዞታ ሟች አባ ኃ/ስላሴ መገኖ ለተጠሪ በኑዛዜ መስጠታቸውን፤ ለተጠሪ በተላለፈው ይዞታ ውስጥ ያለውን የዘይት መጭመቂያ ንግድ ሟች አቶ ኤፍሬም ጌታነህ በኪራይ ሲገለገሉ መቆየታቸውን በማረጋገጥ፤ ይህን ይዞታ ሟች አቶ ኤፍሬም ጌታነህ በሽያጭ ውል የተገኘ በማስመሰል ለስር 5ኛ እና 6ኛ ተከሳሾች በማቅረብ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ መውሰዳቸውን ድምዳሜ ላይ በመድረስ ይዞታው የተጠሪ ነው፤ አቶ ኤፍሬም ጌታነህ በይዞታው ላይ ካርታ የወሰዱት በ19/6/1955ዓ.ም ተደርጓል የተባለን የሽያጭ ውል በማቅረብ መሆኑን በመግለጽ ይህ ውል ደግሞ ያልተደረገ እና በሀሰት የተዘጋጀ መሆኑን በፍሬነገር ደረጃ በማረጋገጥ በይዞታው ላይ ለአቶ ኤፍሬም ጌታነህ ተሰጥቶ የነበረው የባለይዞታነት ሰነድ ሊሰረዝ ይገባል በማለት የሰጠው ውሳኔ እና ይህንኑ ውሳኔ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት በማጽናት የሰጠውን ውሳኔ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 246(1) የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ (እንዳለ) ከተወሰነ በኋላ ፍርድቤቱ ባለጉዳዩቹን የሚከራከረው የተለያዩበት የሕግ ወይም የፍሬነገር አግባብ ምን እንደሆነ በማረጋገጥ ለጉዳዩ ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት የሚስችለውን ጭብጥ በመያዝ ነው በማለት ደንግጓል፡፡ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1815 (1) እና(2) አንድ ውለታ ሲሰረዝ ወይም ሲፈርስ ተዋዋዮቹ በተቻለ መጠን ውለታ ከመደረጉ በፊት እንደነበሩት ሁኔታ

እንዲመለሱ ማድረግ ይገባቸዋል፤ ውለታውን ለመፈጸም የተሰራ ስራ ሁሉ ቀሪ ሆኖ በማናቸውም አኳኋን ውጤት የሌለው ይሆናል በማለት ደንግገዋል፡፡ በቅን ልቡና ለሆነ ሶስተኛ ወገን የተሰራው ስራ ውጤት ጠቃሚ ከሆነ እንደረጋ እንደሚቀር በፍ/ብ/ህ/ቁ 1816 ተመልክቷል፡፡ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1817(1) ውለታውን ለመፈጸም የተሰራውን ስራ ለማፍረስ የማይቻል ሲሆን ወይም አስቸጋሪ ሆኖ ሲገኝ ወይም ከፍ ያለ መሰናክል የሚያመጣ ሲሆን እነዚህ የተሰሩት ስራዎች እንደረጉ እንዲቀሩ ይደረጋል በማለት ደንግጓል፡፡ የዚሁ አንቀጽ ንኡስ ቁጥር 2 እንዲሁም በሆነ ግዜ ዳኞች ተገቢ መስሎ እንደታያቸው ኪሳራ በማስከፈል ወይም ሌላ ውሳኔ በማድረግ በተቻለ መጠን ተዋዋዮቹን ውሉ ከመደረጉ በፊት እንደነበሩት ሁኔታ ለማድረግ ይችላሉ በማለት ደንግጓል፡፡

ውሉ እንዲፈርስ ከተወሰነ በኋላ ተዋዋዮቹ ወደነበሩበት እንዲመለሱ የሚወሰነው በውሉ መሰረት የተሰራውን ስራ ለማፍረስ የማይቻል ወይም አስቸጋሪ ካልሆነ ስለመሆኑ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 15551(ቅጽ3) የፍ/ብ/ህ/ቁ 1716፤ 1815-1817ን ድንጋጌዎች በማጣቀስ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 37391 ፍርድቤቶች የቀረበላቸውን ክርክር መሰረት በማድረግ አግባብነት ያለውን ጭብጥ ሳይመሰርቱ የሚሰጡት ውሳኔ ህጋዊ ነው ሊባል የማይችል ስለመሆኑ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

ገዢ ግዢ ሲፈጽም አንድ ጠንቃቃ ገዢ በሕግም ሆነ በአሰራር ሊያደርገው የሚገባውን ጥንቃቄ የማድረግ ሀላፊነት ያለበት ስለመሆኑ፤ የሽያጭ ውሉም የሚጸናው ገዢው ግብይቱን የፈጸመው አንድ ጠንቃቃ ገዢ እንዲያደርግ የሚጠበቅበትን ጥንቃቄ እና የማጣራት ተግባር ማከናወኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥሮች 198402፤185049፤ 131282 በሰጠው ውሳኔ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ የአንድ ጠንቃቃ ገዢ መለኪያ መስፈርት ምንድን ነው? የሚለውን ነጥብ በተመለከተ አንድ ንብረትን የሚገዛ ሰው ግብይቱን ከመፈጸሙ በፊት የንብረቱ ሻጭ በንብረቱ ላይ ባለመብት ነው አይደለም? የሚለውን ጉዳይ በቅድሚያ የማጣራት ተግባር ዋነኛው ነው ፡፡

በያዝነው ጉዳይ የስር የፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ይዞታ በተመለከተ በሟች አቶ ኤፍሬም ጌታነህ እና በ2ኛ አመልካች መካከል በ15/12/05ዓ.ም የተደረገው የሽያጭ ውል ህገወጥ በመሆኑ ሊሰረዝ ይገባል፤ ለ2ኛ አመልካችም በይዞታው ላይ የተሰጠው ካርታ በስር 5ኛ እና 6ኛ ተከሳሾች እንዲሰረዝ እና በምትኩ በይዞታው ላይ ለተጠሪ አዲስ የባለቤትነት ካርታ እንዲሰጥ፤ በይዞታው ላይ ያለውን ግንባታ በተመለከተ በስምምነት በሚያቀርቡት ግምት፤ መስማማት ካልቻሉ በገለልተኛ ባለሙያ በሚቀርብ የገበያ ግምት መሰረት ተጠሪ ግምቱን ከፍላ ህንጻውን እንድታስቀር፤ ተጠሪ ግምቱን ከፍላ ማስቀረት ያልቻለች ወይም ያልፈለገች እንደሆነ 2ኛ አመልካች ግምቱን በመክፈል እንዲያስቀረው በማለት ለሰጠው ውሳኔ ምክንያት ያደረገው ሟች አቶ ኤፍሬም ጌታነህ ይዞታውን ለ2ኛ አመልካች ያስተላለፉት በይዞታው ላይ መብት ሳይኖራቸው በመሆኑ በሚል ነው፡፡ ሆኖም ፍርድቤቱ እዚህ ድምዳሜ ላይ ከመድረሱ በፊት

በቅድሚያ 1ኛ. 2ኛ አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ይዞታ በ15/12/05ዓ.ም በተደረገ ውል ከአቶ ኤፍሬም ጌታነህ የገዛው አንድ ጠንቃቃ ገዢ የማይንቀሳቀስ ንብረት ግዢውን ከመፈጸሙ በፊት እንዲያደርግ በህጉ የሚጠበቅበትን ጥንቃቄ አድርጎ ነው ወይንስ አይደለም? ይኀውም በቅድሚያ ሻጩ አቶ ኤፍሬም ጌታነህ በይዞታው ላይ ባለመብት ናቸው ወይንስ አይደሉም? የሚለውን አጣርቶ ነው ወይንስ አይደለም? 2ኛ. ከዚህ አንጻርስ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ይዞታ በተመለከተ በአቶ ኤፍሬም ጌታነህ እና በ2ኛ አመልካች መካከል በ15/12/05ዓ.ም የተደረገው የሽያጭ ውል ፈራሽ ሊሆን ይገባል ወይንስ አይገባም? 3ኛ. ውሉ ፈራሽ ሊሆን ይገባል ከተባለስ 2ኛ አመልካች በስር ፍርድቤት ካቀረበው ክርክር አንጻ በይዞታው ላይ በ2ኛ አመልካች የተገነባ ግንባታ መኖሩን በመሆኑ ከዚህ አንጻር በ2ኛ አመልካች በይዞታው ላይ የተገነባውን የግንባታ ዓይነት፣ ደረጃ/መጠን ከግምት ውስጥ በማስገባት በፍ/ብ/ህ/ቁ 1817 ድንጋጌ መሰረት ግራቀኙን ከውሉ በፊት ወደነበሩበት ሁኔታ መመለስ ይቻላል ወይንስ አይቻልም? የሚሉትን ነጥቦች በጭብጥነት ሊይዝ እና ጉዳዩን ግራቀኙ ካደረጉት ክርክር አንጻር እንዲሁም የቀረቡት ማስረጃዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በሌሎች በተገቢዎቹ መንገዶች ሁሉ በማጣራት እና በመመርመር ተጠሪ በሟች አቶ ኤፍሬም ጌታነህ እና በስር 4ኛ ተከሳሽ(2ኛ አመልካች) መካከል በ15/12/2005ዓ.ም የተደረገው ውል እንዲሰረዝ፣ የስር 5ኛ ተከሳሽ አለአግባብ በሰጠው መረጃ መሰረት ለስር 4ኛ ተከሳሽ(2ኛ አመልካች) የተሰጠው ካርታ እንዲሰረዝ፣ በምትኩ የስር 5ኛ እና 6ኛ ተከሳሾች ለይዞታው ለተጠሪ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንዲሰጡ፣ በይዞታው ላይ ያለን ንብረት 2ኛ አመልካች አንስቶ ይዞታውን ለተጠሪ እንዲያስረክብ እንዲወሰን በማለት ባቀረበችው የዳኝነት ጥያቄ ላይ ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ ሊሰጥ ሲገባው ከላይ የተጠቀሱትን ጭብጦች ሳይመሰርት እና በዛው አግባብ ጉዳዩን ግራቀኙ ካደረጉት ክርክር አንጻር እንዲሁም የቀረቡትን ማስረጃዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በሌሎች በተገቢዎቹ መንገዶች ሁሉ ሳያጣራ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ይዞታ በተመለከተ በሟች አቶ ኤፍሬም ጌታነህ እና በ2ኛ አመልካች መካከል በ15/12/05ዓ.ም የተደረገው የሽያጭ ውል ህገወጥ በመሆኑ ሊሰረዝ ይገባል፣ ለ2ኛ አመልካችም በይዞታው ላይ የተሰጠው ካርታ በስር 5ኛ እና 6ኛ ተከሳሾች እንዲሰረዝ እና በምትኩ በይዞታው ላይ ለተጠሪ አዲስ የባለቤትነት ካርታ እንዲሰጥ፣ በይዞታው ላይ ያለውን ግንባታ በተመለከተ በስምምነት በሚያቀርቡት ግምት፣ መስማማት ካልቻሉ በገለልተኛ ባለሙያ በሚቀርብ የገበያ ግምት መሰረት ተጠሪ ግምቱን ከፍላ ህንጻውን እንድታስቀር፣ ተጠሪ ግምቱን ከፍላ ማስቀረት ያልቻለች ወይም ያልፈለገች እንደሆነ 2ኛ አመልካች ግምቱን በመክፈል እንዲያስቀረው በማለት የሰጠው ውሳኔ እና ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ከላይ በተገለጸው መልኩ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤትን ውሳኔ ሊያርም ሲገባው ውሳኔውን በማሻሻል ተጠሪ የግንባታውን ግምት መክፈል ካልቻለች ወይም ካልፈለገች ግምቱን የስር 4ኛ ተከሳሽ(2ኛ አመልካች) ለተጠሪ ከፍሎ እንዲያስቀረው በማለት የሰጠውን የውሳኔ ክፍል በመሻር፣ ቀሪውን የስር ፍርድቤት ውሳኔ( የስር ፍርድቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን ውድቅ በማድረግ ከሰጠው ብይን፣ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ የተጠሪ ነው፣ ለአቶ ኤፍሬም ጌታነህ ተሰጥቶ የነበረው የባለይዞታነት ሰነድ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ከሰጠው

ውሳኔ ውጪ) በማጽናት የሰጠው ውሳኔ ሊታረም የሚገባው መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ይህ ችሎት አግኝቶታል፡፡ ስለሆነም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት በመዝገብ ቁጥር 262376 በ27/7/14ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 226382 በ29/7/2015ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሻሽለዋል፡፡
2. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት በመዝገብ ቁጥር 262376 በ2/10/13ዓ.ም የሰጠው ብይን እንዲሁም በ27/7/14ዓ.ም ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ የተጠሪ ነው፤ ለአቶ ኤፍሬም ጌታነህ ተሰጥቶ የነበረው የባለይዞታነት ሰነድ ሊሰረዝ ይገባል በማለት የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 226382 በ29/7/2015ዓ.ም የፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት በመዝገብ ቁጥር 262376 በ2/10/13ዓ.ም የሰጠውን ብይን እንዲሁም በ27/7/14ዓ.ም ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ የተጠሪ ነው፤ ለአቶ ኤፍሬም ጌታነህ ተሰጥቶ የነበረው የባለይዞታነት ሰነድ ሊሰረዝ ይገባል በማለት የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ጸንተዋል፡፡
3. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት በመዝገብ ቁጥር 262376 በ27/7/14ዓ.ም ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ይዞታ በተመለከተ በሚች አቶ ኤፍሬም ጌታነህ እና በ2ኛ አመልካች መካከል በ15/12/05ዓ.ም የተደረገው የሽያጭ ውል ህገወጥ በመሆኑ ሊሰረዝ ይገባል፤ ለ2ኛ አመልካችም በይዞታው ላይ የተሰጠው ካርታ በስር 5ኛ እና 6ኛ ተከሳሾች እንዲሰረዝ እና በምትኩ በይዞታው ላይ ለተጠሪ አዲስ የባለቤትነት ካርታ እንዲሰጥ፤ በይዞታው ላይ ያለውን ግንባታ በተመለከተ በስምምነት በሚያቀርቡት ግምት፤ መስማማት ካልቻሉ በገለልተኛ ባለሙያ በሚቀርብ የገበያ ግምት መሰረት ተጠሪ ግምቱን ከፍላ ህንጻውን እንድታስቀር፤ ተጠሪ ግምቱን ከፍላ ማስቀረት ያልቻለች ወይም ያልፈለገች እንደሆነ 2ኛ አመልካች ግምቱን በመክፈል እንዲያስቀረው በማለት የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 226382 በ29/7/2015ዓ.ም የፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት በመዝገብ ቁጥር 262376 በ27/7/14ዓ.ም ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ይዞታ በተመለከተ በሚች አቶ ኤፍሬም ጌታነህ እና በ2ኛ አመልካች መካከል በ15/12/05ዓ.ም የተደረገው የሽያጭ ውል ህገወጥ በመሆኑ ሊሰረዝ ይገባል፤ ለ2ኛ አመልካችም በይዞታው ላይ የተሰጠው ካርታ በስር 5ኛ እና 6ኛ ተከሳሾች እንዲሰረዝ እና በምትኩ በይዞታው ላይ ለተጠሪ አዲስ የባለቤትነት ካርታ እንዲሰጥ በማለት የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት እንዲሁም ተጠሪ ግምቱን ከፍላ ማስቀረት ያልቻለች ወይም ያልፈለገች እንደሆነ 2ኛ አመልካች ግምቱን በመክፈል እንዲያስቀረው በማለት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽረዋል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

4. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት የዘጋውን የመዝገብ ቁጥር 262376 የሆነውን መዝገብ አንቀሳቅሶ 1ኛ. 2ኛ አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ይዞታ በ15/12/05ዓ.ም በተደረገ ውል ከአቶ ኤፍሬም ጌታነህ የገዛው አንድ ጠንቃቃ ገዢ የማይንቀሳቀስ ንብረት ግዢውን ከመፈጸሙ በፊት እንዲያደርግ በህጉ የሚጠበቅበትን ጥንቃቄ አድርጎ ነው ወይንስ አይደለም? ይኀውም በቅድሚያ ሻጩ አቶ ኤፍሬም ጌታነህ በይዞታው ላይ ባለመብት ናቸው ወይንስ አይደሉም? የሚለውን አጣርቶ ነው ወይንስ አይደለም? 2ኛ. ከዚህ አንጻርስ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ይዞታ በተመለከተ በአቶ ኤፍሬም ጌታነህ እና በ2ኛ አመልካች መካከል በ15/12/05ዓ.ም የተደረገው የሽያጭ ውል ፈራሽ ሊሆን ይገባል ወይንስ አይገባም? 3ኛ. ውሉ ፈራሽ ሊሆን ይገባል ከተባለስ 2ኛ አመልካች በስር ፍርድቤት ካቀረበው ክርክር አንዱ በይዞታው ላይ በ2ኛ አመልካች የተገነባ ግንባታ መኖሩን በመሆኑ ከዚህ አንጻር በ2ኛ አመልካች በይዞታው ላይ የተገነባውን የግንባታ ዓይነት፤ ደረጃ/መጠን ከግምት ውስጥ በማስገባት በፍ/ብ/ህ/ቁ 1817 ድንጋጌ መሰረት ግራቀችን ከውሉ በፊት ወደነበሩበት ሁኔታ መመለስ ይቻላል ወይንስ አይቻልም? የሚሉትን ነጥቦች በጭብጥነት በመያዝ እና ጉዳዩን ግራቀኙ ካደረጉት ክርክር አንጻር እንዲሁም የቀረቡት ማስረጃዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በሌሎች በተገቢዎቹ መንገዶች ሁሉ በማጣራት እና በመመርመር ተጠሪ በሚች አቶ ኤፍሬም ጌታነህ እና በስር 4ኛ ተከሳሽ(2ኛ አመልካች) መካከል በ15/12/2005ዓ.ም የተደረገው ውል እንዲሰረዝ፤ የስር 5ኛ ተከሳሽ አለአግባብ በሰጠው መረጃ መሰረት ለስር 4ኛ ተከሳሽ(2ኛ አመልካች) የተሰጠው ካርታ እንዲሰረዝ፤ በምትኩ የስር 5ኛ እና 6ኛ ተከሳሾች ለይዞታው ለተጠሪ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንዲሰጡ፤ በይዞታው ላይ ያለን ንብረት 2ኛ አመልካች አንስቶ ይዞታውን ለተጠሪ እንዲያስረክብ እንዲወሰን በማለት ባቀረበችው የዳኝነት ጥያቄ ላይ ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ ሊሰጥ ይገባል በማለት ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 343(1) መሰረት መልሰንለታል፡፡
5. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍርድቤቶች ይድረሳቸው፡፡
6. መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ወደመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

የሰበር መዝገብ ቁጥር - 247036

ቀን - 24/04/2017 ዓ.ም

ዳኞች - ሽመክት አሰፋ

እንዳሻው አዳነ

አለማየሁ ሹናራ

ዋዚሞ ዋሲራ

ዘውዲቱ ታደሰ

አመልካች - ሲቀላ ክፍለ ከተማ ማዘጋጃ ቤት - የቀረበ የለም

ተጠሪ - ወ/ሮ አረግዋ ጠብቀው - የቀረበ የለም ከተባለ በኃላ ሽመልስ እንግዳ ቀረቡ

መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው ለምርመራ ስለሆነ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የተጀመረው በቀድሞ ደቡብ ብሄረሰቦች ህዝቦች ክልል መንግስት የአርባምንጭ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች ተከሳሽ ተጠሪ ከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የስር ከሳሽ በአመልካች ላይ ያቀረቡት ክስ ዝርዝር ይዘቱ በአጭሩ ባለቤታቸው የ ፶ አለቃ እንግዳ ንጉሴ በህይወት በነበረበት ጊዜ በመለያ ቁጥር 207 የሚታወቅ 625 ካሬ ሜትር ስፋት ያለው ይዞታ ከወ/ሮ ተፈሪ ወልደጊዮርጊስ የገዙ መሆኑን በመሬቱ ላይ ግብር እስከ 2007 ዓ.ም ድረስ የተከፈለ ቢሆንም የይዞታ ባለቤትነት ወደ አመልካች እና ሌሎች ወራሾች ስም እንዲዞርላቸው ያቀረብነው

ጥያቄ ተከሳሽ ፍቃደኛ ባለመሆኑ የባለቤትነት ስም ወደ ከሳሽ ስም እንዲያዞር እንዲወሰን የሚል ነው፡፡

ተከሳሽ ለክሱ የሰጠው መልስ ጉዳዩ በአስተዳደር በኩል ውሳኔ የሚሰጥበት የአስተዳደራዊ ጉዳይ ነው፡፡

ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የለውም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና በአማራጭ መልስ ካቀረቡ በኃላ ፍርድ ቤቱ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያውን ውድቅ በማድረግ ተከሳሽ ስም ለማዞር ይገደዳል ወይስ አይገደድም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መዝገቡን መርምሮ በ27/01/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተከሳሽ ስም ወደ ከሳሽ ለማዞር አይገደድም ብሎ ብይን ሰጥቶ ይህ ብይን እስከ ክልሉ ሰበር ድረስ ቢፀናም የአሁኑ ተጠሪ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቅሬታ በማቅረባቸው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 206676 በቀን 29/02/2014 አ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔን በመሻር የአርባ ምንጭ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በብይን የዘጋውን መዝገብ ቁጥር 29573 እንደገና በማንቀሳቀስ የያዘውን የክርክር ጭብጥ ላይ የግራ ቀኙን ማስረጃ አድምጦና መርምሮ የመሰለውን እንዲወስን መዝገቡን መልሶታል፡፡

መዝገቡ ከተመለሰ በኃላ በድጋሚ የአርባ ምንጫ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት ሙሉ ለሙሉ የተወረሰ ነው ወይስ በከፊል የተወረሰ ነው? በከፊል የተወረሰ ከሆነ የሟች ያልተወረሰ ቦታ ስንት ካሬ ሜትር እና ስንት ክፍል ቤት ነው? ያልተወረሰ እና በሟች ስም ያለው ቦታ በአመልካች ወ/ሮ አረጋ ጠብቀው ስም ሊዞር ይገባል ወይስ አይገባም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ የምስክሮች ቃል ሰምቷል፡፡ የከሳሽ ምስክሮች ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታው ስፋት 625 ካሬ ሜትር መሆኑን ይዞታው በሟች ፶ አለቃ እንግዳ ንጉሴ ስም የነበረ መሆኑን አሁን በባለቤታቸው እጅ ያለው መሆኑን ተከሳሽ ወደ ከሳሽ ስም ለማዞር ፍቃደኛ ያለመሆኑን የከሳሽ ቤት ቀበሌ ያልወረሰው መሆኑን በግቢ ውስጥ የቀበሌ ቤት ያለመሆኑን ተከሳሽ የቀበሌ ቤት እያለ የይዞታ ማረጋገጫ አልሰጥም መላቱን በ1970 ዓ.ም ቀበሌው ትርፍ ቤት ነውሁለት ለሌላ ሰው ማከራየቱን ቀበሌ በትርፍ ቤትነት ይዘው ያስገቡት ሁነት ቤት የተከራየው ሰው አፍርሶ ለማሰራት ሲል ቀበሌው መከልከሉን አንዱ ውስጥ የቀበሌ ተከራይ መኖሯዋን ዋናው ቤት ውስጥ ከሳሽና ቤተሰቦች መኖሯቸውን ሰርቪስ ቤት ጋር ያለበት የፈረሰ ቤትና አንድ ክፍል የተከራየበት ሰው መኖሩን ከሳሽ የያዘችበት ቤት ቀበሌ ለይቶ የሰጠው ነገር ስለሌለ መንግስት ግብር አንቀበልም ያሉበት በዚህ ምክንያት ነው በማለት የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተዋል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

የተከሳሽ ምስክሮች ያልቀረቡ ስለሆነ ማስረጃ የማሰማት መብታቸው ታልፏል፡፡ የችሎቱ ዳኛ እስከ ቦታው ድረስ በመሄድ አጣርቷል፡፡ ዳኛው እስከ ቦታው ድረስ ሄደው ያጣራው ውጤት በቦታው የከሳሽ ቤት እና መንግስት ቤት መኖሩን አረጋግጧል፡፡ የማዘጋጃ ቤት ባለሞያ ቀበሌ የሚያስተዳድረውና ከሳሽ የሚያስተዳድሩት ስንት ካሬ ሜትር እንደሆነ ለክቶ ውጤቱን እንዲገልፅ ባዘዘው መሰረት ባለሞያ ለክቶ ሪፖርት ለፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ በሪፖርቱ ላይ ከሳሽና ተከሳሽ አስተያየት እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ከሳሽ የሰጡት አስተያየት የቀበሌ ቤት የፈረሰ በመሆኑ ክፍት ቦታ የቀበሌ ነው ሊባል አይገባም የቀበሌ ነው ቢባል እንኳን ቤቱ የተሰራበት ቦታ ብቻ 100.4 ካሬ ሜትር ብቻ የቀበሌ ነው ተብሎ ከ 658 ውስጥ ተቀንሶ ቀሪ ይዞታ በከሳሽ ስም ተመዝግቦ የይዞታ ማረጋገጫ እንዲሰጠኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡ የግራ ቀኙ የሰውና የሰነድ ማስረጃ ቃል ፍርድ ቤቱ በመመርመር በአከራካሪው ይዞታ ውስጥ ሁለት ክፍል የመንግስት ቤት መኖሩና መንግስት እያከራየ ኪራይ የሚሰበስብበት ቤት የውርስ ቤት መኖሩ ስለተራጋገጠ በከፊል የተወረሱ ቤቶች መኖራቸው ተረጋግጧል፡፡ በሟች ስም ያለው ያልተወረሰ ይዞታ መጠን በተመለከተ በወቅቱ አንድ ክፍል ቤት ለከሳሽና ለቤተሰቦች እንደተተወ ሁለት ክፍል ቤት ተወርሶ ቀበሌ እያስተዳደረው የነበረ መሆኑን የቀበሌ ሁለት ክፍል ውስጥ አንድ ክፍል በእርጅና ምክንያት መፍረሱ ተረጋግጧል፡፡

የቀበሌ ቤት ያረፈበት ቦታ ስፋቱ 108 ካሬ ሜትር መሆኑ በባለሞያ ልኬት የተረጋገጠ ስለሆነ 108 ካሬ ሜትር ተቀንሶ ቀሪ ይዞታ በከሳሽ ስም የይዞታ ማረጋገጫ ሊሰጥ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኝ ቅሬታ ለጋሞ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ፍርድ ቤቱ ይግባኝ ቅሬታቸውን ባለመቀበል መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ በመቀጠል አመልካች ሰበር ቅሬታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም መሰረታዊ የህግ ስህተት አልተገኘም በማለት ዘግቶታል፡፡

የአሁን ሰበር ቅሬታ የቀረበው ይህን የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ የሰበር ቅሬታ ይዘቱ በአጭሩ በሟች ስም የተመዘገበ ቤትና ይዞታ ያለመኖሩ እየታወቀ በጉዳዩ ላይ ስልጣን ሳይኖር በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት ትርፍ ቤትና ይዞታ ተወርሶ እያለ ቤቱን ብቻ መወሰናቸው በከፊል የተወረሰ የመንግስት ቤት ካለ የስም ዝውውር ሊደረግ ይገባል አይገባም የሚለው በአግባቡ ሳይመረመር ከ 656 ካሬ ሜትር ውስጥ 550 ካሬ ሜትር በተጠሪ ስም እንዲዞር መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፡፡

ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤትና ይዞታ በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት መውረሱ በማስረጃ ተረጋግጦ እያለ ካሉት ሶስት ዳጃፎች ቤት ሁለት ደጃፍ ትርፍ ቤትንና መሬትን መወሰን ሲገባው ቤቱን ብቻ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት ትርፍ ቤት እና መሬት የተወረሰ መሆኑ በማስረጃ ከተረጋገጠ ትርፍ የሆነውን ቤትና ይዞታ እንዲለካ ማዘዝ ሲገባው ከአዋጅ ቁጥር 47/67 መንፈስ ውጪ የመንግስት ቤት ብቻ ያለውን እንዲለካ ማዘዙ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፡፡

የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ በሟች ፱ አለቃ እንግዳ ንጉሴ ስም ተመዝግቦ ያለው ቤት በስሜ እንዲዞር የሚል ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤቶች በተጠሪ ባለቤት ስም መኖር አለመኖር በማስረጃ አረጋግጦ መወሰን ሲገባው ያልተጠየቀ ዳኝነት ካርታ ተሰርቶ እንዲሰጥ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት የተወረሰ የመንግስት ቤት በስም ዝውውር ሽፋን ይመለስልኝ ጥያቄ ለፍርድ ቤት ሳይሆን ለፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ የሚቀርብ ጉዳይ ስለሆነ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን የስረ ነገር ስልጣን ሳይኖረው የውሰነ በመሆኑ ስህተት ነው፡፡

ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታና ቤት በሟች ፱ እንግዳ ንጉሴ ስም ያልተመዘገበ በመሆኑ አሁን በተጠሪ ስም እንዲመዘገብ መወሰኑ ስህተት ነው፡፡ ተጠሪ ስም ዝውውር ይደረግልኝ ጥያቄ አቅርበው የስር ፍርድ ቤት ካርታ ተሰርቶ እንዲሰጥ የሰጠው ውሳኔ ያልተጠየቀ ዳኝነት ስለሆነ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ተሽሮ እንዲወሰን የሚል ነው፡፡

ይህ ችሎት የክልሉ ፍርድ ቤቶች አመልካች የመለያ ቁጥር 207 ካሬ ሜትር ከሆነው 658.6 ካሬ ሜትር ላይ ካሉት ሶስት ክፍል ቤቶች ውስጥ አንድ ክፍል ቤት በ 550 ካሬ ሜትር ጋር በአዋጅ ቁጥር 47/67 ያልተወረሰ የተጠሪ አውራሽ ቤት ስለሆነ አመልካች ወደ ተጠሪ ስም አዛውሮ እንዲመዘግብ ሲወስን የተወረሱ ሁለት ክፍል ቤቶች ናቸው ለተባሉ ሁለት ክፍል ቤቶች በተነፃፀሪ ሊደርሰው የሚገባ የመሬት ስፋት በአግባቡ ተጣርቶ የተወሰነ ነው ወይ? የሚለውን አከራካሪ ፍሬ ነገር በማስረጃ አረጋግጦ ከመወሰን የክርክር አመራር አኳያ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 232290 (ያልታተመ)፣ 22603 (በቅፅ 6) እና 105956 (ቅፅ 20) ላይ ከተሰጠው የህግ ትርጉም አንፃር በአዋጅ ቁጥር 47/67 አንቀፅ 2(3)(ሀ) እና (4) እና አንቀፅ 5(1) አተገባበር አንፃር እንዲሁም መንግስት በአዋጅ የወረሰውን መኖሪያ ቤት በመኖሪያ ቤትነት ለመገልገል ከሚያስፈልገው የመሬት ይዞታ ላይ የሚኖረውን የንብረት መብት የህገ መንግስቱ አንቀፅ 40 መሰረት በማድረግ ተጠሪ የሚያቀርቡት ክርክር ተሰምቶ ለመወሰን በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 2(4)(ሀ) እና (ሸ) እና 10(1)(ሐ) እና (መ) እንዲሁም በሰበር ስነ ስርአት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 7(3) ስር በተደነገገው መሰረት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ በመታዘዙ ምክንያት ተጠሪ በ 21/08/2016 ኢ.ም 04 ገፅ አቅርበው ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

ይዞቱ በአጭሩ የቦታ መለያ ቁጥር 207 ስፋቱ 625 ካሬ ሜትር በባለቤቴ የ፶ አለቃ እንግዳ ንጉሴ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ስለመሆኑ ከ 1965 ኢ.ም እስከ 2007 ኢ.ም ድረስ የቦታ፣ የቤት ጣሪያና ግድግዳ ግብር በባለቤቴ ስም የሚከፈል ስለመሆኑ የግብር ካርኒዎች በማስረጃነት የቀረበ መሆኑን፣ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ ላይ ሁለት ክፍል የአመልካች ያለ ቢሆንም አንድ ክፍል ቤት በእርጅና ምክንያት ፈርሶ አንድ ክፍል ቤት ብቻ የቀረ በመሆኑ የቀረውና የፈረሰው ቤት እኩል ስፋት ስላላቸው ያልፈረሰው ቤት ተለክቶ 54 ካሬ ሜትር በመሆኑ ሁለቱ ተመሳሳይ ስፋት ስላላቸው 108 ካሬ ሜትር መሆኑ በባለሞያ ተረጋግጦ በቀረበው ሪፖርት መሰረት ስር ፍርድ ቤት በ550.6 ካሬ ሜትር ይዞታ ላይ ስም በተጠሪ ስም እንዲዛወር መወሰኑ በአግባቡ መሆኑን፤ በአመልካች የተወረሰ ሁለት ክፍል ቤቶች ያረፉበት ይዞታ መጠንና በተጠሪ እጅ የሚገኝ የመኖሪያ ቤትና የሰርቪስ ቤቶች ያሉበት ይዞታ መጠኑ ምን ያህል እንደሆ የመንግስት ተቋም የሆነው የከተማ ማዘጋጃ ቤት ባለሞያዎች ለክተው አጣርተው ባቀረቡት ሪፖርት መሰረት የተሰጠ ውሳኔ ስለሆነ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም ተብሎ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲፀናልኝ የሚል ነው፡፡

አመልካች በ 02/09/2016 ዓ.ም በ 02 ገፅ የመልስ መልሳቸውን የሰበር ቅሬታቸውን በማጠናከር አቅርበው ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ በተዘረዘረው መሰረት በመጠቃለሉ እኛም ለሰበር ቅሬታ መነሻ የሆነውን ፍርድ፣ በግራ ቀኙ በኩል የቀረበውን ክርክር እንዲሁም ይህ ሰበር ችሎት በማስቀረቢያነት ከያዘው ጭብጥ አንፃር በአመልካች በኩል የተወረሰው ቤቶች ሁለት ክፍል ሲሆኑ በተጠሪ እጅ የሚገኝ ያልተወረሰ ቤት አንድ ክፍል ሆኖ እያለ አመልካች ለተጠሪ ስፋቱ 625 ካሬ ሜትር ውስጥ 108 ካሬ ሜትር ቀንሶ በቀረው ላይ ለተጠሪ የይዞታ ማረጋገጫ እንዲሰጥ ስም ዝውውወርም ወደ ተጠሪ እንዲያዞር ሲል የወሰነበት አግባብ ከሰበር መዝገብ ቁጥር 232290፣ 22603 እና 105956 አንፃር አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

መርምረን እንደተረዳነው ከሆነ የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ በባለቤቴ ስም የሚታወቅ ቤት ባለቤቴ ስለሞተ የይዞታ ባለቤትነት ስም ወደ እኔ እንዲያዞር ተብሎ እንዲወሰን የሚል ነው፡፡ አመልካች ይዞታውና ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት ትርፍ ቤትና ቦታ ተብሎ የተወረሰ ስለሆነ ወደ ተጠሪ ስም ሊዞር አይችልም በማለት ተከራክሯል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ

ችሎት በሰጠው ውሳኔ መሰረት የስር ወረዳ ፍርድ ቤት መዝገቡን አንቀሳቅሶ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት የተወረሰ ቤት አለ ወይ? ካለ ስንት ክፍል ነው? ስንት ካሬ ሜትር ነው የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ማስረጃ ሰምቶ የተወረሰው ቤት መኖሩን የችሎቱ ዳኛ እስከ ቦታው ድረስ ወርዶ አጣርተው ሁለት ክፍል ቤት መንግስት ወርሶ እያስተዳደረ መሆኑን አንዱ ክፍል ቤት በእርጅና ምክንያት መፍረሱን አንዱ ክፍል ቤት ያልፈረሰና መንግስት እያከራየ ከኪራይ ገቢ እየገኘ ያለመሆኑ የፈረሰውና ያስፈረሰው ቤት ስፋቱ እኩል በመሆኑ እያንዳንዱ ቤት ስፋቱ 54 ካሬ ሜትር መሆኑ ሁለት ክፍል ቤት ስፋቱ 108 ካሬ ሜትር መሆኑን በማረጋገጥ ከባለሞያ መግለጫ ከቀረበ በኃላ የስር ፍርድ ቤት በመንግስት የተወረሰው ሁለት ክፍል ቤት በመሆኑ ያልተወረሰው በከሳሽ እጅ ያለው ቤት አንድ ክፍል ቤት መሆኑን የሁለት ክፍል ቤት ስፋት 108 ካሬ ሜትር በመሆኑ 105 ካሬ ሜትር ከተቀነሰ በኃላ ቀሪ ይዞታ ላይ ለተጠሪ ስም ዝውውር እንዲፈፀም ሲል ወስኖ ይህ ውሳኔ እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ፀንቷል፡፡

የአመልካች ዋነኛው ቅሬታ የተወረሰው ትርፍ ቤት እና ቦታ ሆኖ እያለ የቤቱ ስፋት ብቻ ተለክቶ መወቀሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው በማለት ይከራከራል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት የተወረሰው ትርፍ ቤት እና ይዞታ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ በስር ፍርድ ቤት የታዘዘው የማዘጋጃ ቤት ባለሞያ የለካው ቤትና ቦታ ሳይሆን ሁለት ክፍል ቤቶች ያረፉበት ቦታ ስፋት ብቻ መሆኑን መዝገቡ ያስረዳል፡፡ አንድ መኖሪያ ቤት በከተማ እስታንዳርድ መሰረት መውጫና መግቢያ ቦታ ያለው ማዕድ ቤት ሽንት ቤት መስሪያ ቦታ ያለው መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡ ተጠሪ የያዙት አንድ ክፍል ቤትም በተመሳሳይ ሁኔታ መውጫና መግቢያ ሽንት ቤት እና ማዕድ ቤት የሚሰራበት ቦታ ያለው ሊሆን ይገባል፡፡ ከዚህ አንፃር በአመልካች ስም የሚታወቀው ሁለት ክፍል ቤት ጋር ያለው ቦታ ስፋት እና በተጠሪ ስም ያለው አንድ ክፍል ቤት ጋር ያለው የቦታ ስፋት ተለክቶ ሊታወቅ ይገባል፡፡

በስር ፍርድ ቤት በባለሞያ የተለካው የአመልካች ሁለት ክፍል ቤት ብቻ ነው እንጂ የቦታ ስፋት ምን ያህል እንደሆነ አልተረጋገጠም፡፡ ትክክለኛ አሰራር ሊሆን የሚችለው የአመልካች እና የተጠሪ ቤትና ይዞታ ስፋት በሙሉ መለካት አለበት፡፡ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠው የአመልካች ቤት የተሰራበት ቦታ ብቻ ነው፡፡ መውጫና መግቢያ በር እና የማዕድ ቤት እና ሽንት ቤት ያረፈበት ቦታ ስፋቱ ስንት እንደሆነ አልተረጋገጠም፡፡ የተጠሪ ቤትና ከቤት ጋር መግቢያና መውጫ እና ማዕድ ቤትና ሽንት ቤት ያረፈበት ቦታ ስፋት ስንት እንደሆነ አልተረጋገጠም፡፡

በአጠቃላይ የአመልካች ሁለት ክፍል ቤት ጋር በተያያዘ ያለው የመውጫና መግቢያ በር ቦታ እና ከጓሮ በኩል ለማዕድ ቤትና ሽንት ቤት መስሪያ ቦታ ያለው ስፋት እንዲሁም የተጠሪ አንድ ክፍል ቤት ጋር በተያያዘ መግቢያና መውጫ በር ያለው ቦታ ስፋት እና ማዕድ ቤት እና ሽንት ቤት ያረፈበት ቦታ ስፋት ተለክቶ ሊታወቅ ይገባል፡፡

ከላይ በተዘረዘረው መሰረት በባለሞያ ቤትና ቦታው ተለክቶ ተለይቶ መወሰን ሲገባ የስር ፍርድ ቤት የአመልካች ሁለት ክፍል ቤቶች ያረፉበት ቦታ ብቻ መለካቱ መውጫና መግቢያ በር እና ማዕድ ቤትና ሽንት ቤት መስሪያ ቦታ እንዲያጣ የሚያደርግ ስለሆነ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ሲጠቃለል ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት የተጠሪ ባለቤታቸው ቤት ቢሆንም ትርፍ ቤትና ቦታ ነው ተብሎ በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት ሁለት ክፍል ቤትና ቦታ የተወረሰ መሆኑ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ጉዳይ ስለሆነ ሁለት ክፍል ቤት እና የቦታ ስፋት ምን ያህል እንደሆነ በባለሞያ ልኬቱ ያልተረጋገጠ በመሆኑ የአመልካችና ተጠሪዎች ቤት እና ቦታ ተለክቶ ተለይቶ ሊወሰን የሚገባ በመሆኑ በገለልተኛ ባለሞያ የግራ ቀኙ ወገኖች ቤት እና ቦታ መጠኑ ተለክቶ ከታወቀ በኃላ የተጠሪ ቤትና ይዞታ መጠኑ ተለይቶ ከሟች ባለቤታቸው ስም ወደ ተጠሪ ስም ሊዛወር ይገባል፡፡

በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙ ቤትና ይዞታ ስፋቱ ምን ያህል እንደሆነ በባለሞያ ሳይለካ የአመልካች ቤት ስፋት ብቻ በመለካት ሌላው ቦታ በሙሉ ለተጠሪ ይገባል ብሎ መወሰኑ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 2(4)(ሀ) እና (ሽ) እና 10(1)(ሐ) እና (መ) እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 232290፣ 22603 ቅፅ 6 እና 105956 ቅፅ 20 መሰረት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች ክልል የአርባ ምንጭ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 29573በቀን 14/06/2015 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ፣ የጋሞ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 116739 በቀን 25/07/2015 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 46916 በቀን 19/08/2015 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስነ ስርአት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9(1)(ለ) መሰረት ተሽሯል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

2. የአርባ ምንጭ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተዘጋውን መዝገብ ቁጥር 29573 የሆነውን መዝገብ በማንቀሳቀስ የአመልካች ሁለት ክፍል ቤቶች ጋር ያለው መግቢያና መውጫ በር እና የማዕድ ቤትና ሽንት ቤት ያለው ቦታ ስፋት በተመሳሳይ ሁኔታ የተጠሪ አንድ ክፍል ቤት ጋር በተያያዘ ያለው መግቢያና መውጫ በር እና የማዕድ ቤትና ሽንት ቤት ያለው ቦታ ስፋት በገለልተኛ ባለሞያ ተለክቶ ከታወቀ በኃላ ተገቢው ውሳኔ እንዲሰጥበት በሰበር ስነ ስርአት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9(2) መሰረት መልሰናል፡፡
3. በውሳኔው መሰረት እንዲፈፀም የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡
4. በዚህ ችሎት የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠ እግድ ካለ ተነስቷል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

**ማስታወሻ፡** - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

1ኛ ሰበር ሰሚ ችሎት

የሠ/መ/ቁጥር 248735

ታህሳስ 24 ቀን 2017 ዓ/ም

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 248735

ታህሳስ 24 ቀን 2017ዓ/ም

ዳኞች ፡- ገበየሁ ፈለቀ

ደረጀ አያና

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

ብርሃኑ መንግሥቱ

አመልካች፡- የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ቢሮ ዓቃቤ ህግ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ መዓዛ በልስቲ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

**ፍርድ**

ጉዳዩ ያለደረሰኝ ግብይት የማከናወን የወንጀል ክስን የሚመለከት ሆኖ ክሱ የቀረበው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ደጀን ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን በአመልካች እና በሰበር ክርክሩ የሌሉት ሁለት ግለሰቦች ላይ ቀርቦ የነበረው ክስ፡- የክልሉን የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 አንቀጽ 131/1 እና 119/1 ሥር የተመለከተውን በመተላለፍ በግብር ከፋይ መለያ ቁጥር 0052005902 ፣ በንግድ ምዝገባ ቁጥር AM/EG/DEJEN/1/0001230/2010 በተጠሪ ስም የተመዘገበ በደጀን ከተማ 01 ቀበሌ በሚገኘው ሆቴልና ሉካንዳ ቤት የንግድ ሥራ በደረጃ "ለ" ግብር ከፋይነት ተሰማርተው የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅና ባለቤት ሁነው እየሰሩ እያለ ሚያዝያ 6 ቀን 2014 ዓ.ም ከቀኑ በግምት 5:50 ሰዓት ላይ ደርብ አበጀና አፀደ ከተማው የተባሉ ደንበኞች አንድ በየአይነቱ ምግብ እና አንድ ሊትር የታሸገ ውሃ ተጠቅመው ደርብ አበጀ የተባለው ለተጠቀሙበት ክፍያ ብር 200.00(ሁለት መቶ) ለአስተናጋጅ ሲሰጥ የብር 135.00 (አንድ መቶ ሰላሳ አምስት) ሽያጭ ያለደረሰኝ ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡

ተጠሪም የእምነት ክህደት ቃላቸውን ተጠይቀው ከአዲስ አበባ የሂክምና ቀጠሮ ስለነበራቸው ወንጀሉ ተፈጽሟል በተባለበት ቦታ ያልነበሩ መሆኑን፣ያለደረሰኝ ግብይት ይፈፀም አይፈፀም እንደማያውቁ፣ የድርጅቱን ሥራ በአግባቡ እንዲሰሩ ለሥር ለሥር 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች እንዳሳወቁ ገልጸው ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የዐቃቤ-ሕግ ምስክሮች የሰጡትን የምስክርነት ቃል ሰምቶ ወንጀሉ ተፈጽሟ በተባለት ቀንና ሰዓት ተጠሪ በድርጅቱ ውስጥ አለመኖራቸው በቃቤ-ሕግ ምስክሮች መነገሩን ጠቅሶ አመልካች የሥር 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች በተመደቡበት የስራ ኃላፊነት ብቁ ሠራተኞች መሆናቸውን በማመን ወደ ህክምና የሄዱ መሆኑ ተረጋግጧል በሚል በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 141 መሠረት በነፃ ያሰናበተ ሲሆን፣አመልካች ተጠሪ ከክሱ በብይን በነፃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

መሰናበታቸውን በመቃወም ያቀረበው የይግባኝ አቤቱታ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 195 መሠረት መሰረዙን ተከትሎ አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩ የፌደራል በመሆኑ ለክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ሊቀርብ አይገባም በሚል ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

የሰበር ቅሬታ የቀረበው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩ የፌዴራል ነው በሚል የሰበር አመልካች ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ ባለመቀበል የሰጠውን ፍርድ በመቃወም ሆኖ የሰበር ቅሬታው በአጭሩ፡- ተጠሪ በደጀን ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት በሆቴልና ሉካንዳ ቤት ንግድ ዘርፍ በደረጃ "ለ" በክልል ግብር ከፋይነት ተመዝግበው ሲሰሩ በክልሉ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 240/2008 አንቀፅ 79/2 እንዲሁም በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 አንቀፅ 19/3 የተመለከተውን ደረሰኝ የመስጠት ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 አንቀፅ 131/1 እና 119/1 የተመለከተውን በመተላለፍ በፈፀሙት ወንጀል በደጀን ወረዳ ፍርድ ቤት ክስ ቀርቦባቸው ክርክር ተደርጎ የወረዳው ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣኑ ክርክሩን አይቶ የሰጠውን ውሳኔ የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በይግባኝ ሰሚነቱ የተመለከተውን የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘን የክልል ጉዳይ ተጠሪ በክልሉ የደረጃ "ለ" ግብር ከፋይ እንጅ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ባልሆኑበት በክልል ግብር ከፋይነታቸው ለፈፀሙት የወንጀል ጥፋት ተጠያቂ የሚሆኑት በክልል የታክስ አስተዳደር አዋጅ መሆኑ እየታወቀ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር አጣሪው ችሎት ጉዳዩን የማየት የሥረ-ነገር ሥልጣን የለኝም በማለት አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አለመቀበሉ የአማራ ብሔራዊ ክልል ፍርድ ቤቶችን ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ ቁጥር 223/2007 አንቀፅ 17/1 ፤ እንዲሁም የክልሉን ፍርድ ቤቶች ለማቋቋም ተሻሽሎ የወጣውን አዋጅ ቁጥር 281/2014 አንቀፅ 24 ድንጋጌዎችን የሚቃረን መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት በሰበር ሰሚ ችሎቱ እንዲታረምላቸው ጠይቃዋል፡፡

በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 6/1 መሠረት ለሰበር ሰሚው ችሎቱ የተመራው የሰበር አቤቱታ በሰበር ሰሚ ችሎቱ ተመርምሮ አመልካች ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር አጣሪው ችሎት ያቀረበው አቤቱታ በደጀን ወረዳ ፍርድ ቤት ተጠሪ እና የሥር 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች የክልሉን የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 አንቀጽ 131/1 እና 119/1 ሥር የተደነገገውን ተላልፏል በሚል የመሰረተውን ክስ የወረዳው ፍርድ ቤቱ ተጠሪን በብይን በነፃ ማሰናበቱን ተከትሎ የቀረበ የሰበር አቤቱታ ሆኖእያለ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን እንደ ፌደራል ጉዳይ በመቁጠር ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊቀርብ የሚችል አይደለም በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢነት ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 80/3(ለ) እና

97/4፤ከክልሉ ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 281/2014 አንቀፅ 24/1(ለ) ፤እንዲሁም የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀ 4/10 ጋር አገናዝቦ ለመመርመር ሲባል ያስቀርባ ተብሎ ተጠሪ ተከታዩን መልስ ሰጥተዋል፡፡

ተጠሪ ለሰበር ቅሬታው በሰጡት መልስ፡- የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች ያቀረበውን አቤቱታ ውደቅ ያደረገው የደጀን ወረዳ ፍርድ ቤት ተጠሪ በተከሰሱበት የወንጀል ድርጊት ጥፋተኛ አለመሆናቸውን በማረጋገጥ የሰጠው ውሳኔ በይግባኝ ሰሚው የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በማጽናቱ የተፈፀመ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም በሚል እንጅ ሥልጣን የለኝም በሚል አይደለም፡፡ በወረዳው እና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የታየን ጉዳይ በሰበር ደረጃ ያለ ፍርድ ቤት ሥልጣን የለኝ ሊል የሚችልበት አመክንዮ አለመኖሩን፤ የሥር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን የተመለከቱት ያለ ሥልጣናቸው ቢሆን ኖሮ ያለሥልጣናቸው የሰጡትን ውሳኔ ሽሮ ይመልሳል እንጅ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የለኝም በሚል አለመሆኑን፤የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ውድቅ ያደረገው በሥር ፍርድ ቤቶች የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም በሚል በመሆኑ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለ መልኩ የተመለከተው የግራ ቀኝ ክርክር እና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ውሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንፃር የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች አንፃር ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት በፌዴራል እና በክልሎች የተዋቀረ መሆኑ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐሊክ ሕገ መንግስት አዋጅ ቁጥር 1/1987 አንቀጽ 46/1 እና አንቀፅ 50/1 ሥር ተመልክቷል፡፡ የፌደራል መንግስቱም ሆነ የክልል መንግስት ሥልጣን ምንጭ ሕገ-መንግስት መሆኑን፤ለፌደራሉ መንግስት የተሰጠው ሥልጣን በክልሎች መክበር ያለበት መሆኑን፤ በተመሳሳይ ለክልሎች የተሰጠውን ሥልጣን የፌደራል መንግስት ማክበር እንዳለበት የሕገ-መንግስቱ አንግጽ 50/8 ያመለክታል፡፡ ለሁለቱም መንግስታት የተሰጠው ስልጣንም የህግ አውጪነት፤ የህግ አስፈፃሚነት እና የዳኝነት ስልጣን ስለመሆኑ በአንቀፅ 50/2 ስር ተመልክቷል፡፡ በዚህ መልኩ ለፌዴራል መንግስቱ የተሰጠው ስልጣን በህገ መንግስቱ አንቀፅ 51 ስር የተዘረዘረ ሲሆን ለክልሎች የተሰጠው ስልጣን ደግሞ በአንቀፅ 52 ስር በዝርዝር ተመልክቷል፡፡

የኢትዮጵያ መንግሰት አወቃቀር ፌደራላዊ ከመሆኑ አንፃር የዳኝነት አካሉም በፌደራል እና ክልል ደረጃ የተቋቋመ ቢሆንም ፤ የፍርድ ቤቶቹ አደረጃጀት ትይዩ ባለመሆኑ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች በክልላቸው ከሚሰጣቸው የዳኝነት ሥልጣን በተጨማሪ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሥልጣን

ደርበው የሚሰሩ ሲሆን ፤ የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶችም በክልላቸው ከሚኖራቸው የዳኝነት ሥልጣን በተጨማሪ በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሚታዩ ጉዳዮችን የማየት ሥልጣን አላቸው፡፡ (የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80/2 እና 80/4 ይመለከቷል፡፡) የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 80/3(ሀ) ድንጋጌ መሠረት ማንኛውንም መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበትን የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘን ጉዳይ በሰበር አይቶ የማረም ሥልጣን አለው፡፡

የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበትን በክልል ጉዳዮች ላይ የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔን በሰር ሰሚው ችሎት አይቶ የማረም ሥልጣን አላቸው፡፡ (የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80 (3/ለ) ይመለከቷል፡፡) የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ክልላዊ ጉዳዮችን በተመለከተ የመጨረሻው የዳኝነት አካል መሆኑንና ማንኛውንም በክልላዊ ፍርድ ቤት የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ሲኖርበት በሰር ችሎት የማየት ሥልጣን ያለው መሆኑን የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልል ሕገ- መንግስት ለማጽደቅ የወጣው አዋጅ ቁጥር 59/1994 አንቀጽ 67/2(ሀ እና ሐ) ይደነግጋል፡፡ በተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 281/2014 ቁጥር 24/1(ለ) ድንጋጌ መሠረት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል የሚቀርበውን በክልል የዳኝነት ሥልጣኑ መነሻነት በከፍተኛ ፍርድ ቤት ታይቶ የመጨረሻ ፍርድ፤ውሳኔ፤ብይን፤ ወይም ትዕዛዝ የተሰጠበትን ማንኛውንም ጉዳይ በሰበር አይቶ የማረም ሥልጣን አለው፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት የሕግ ድንጋጌዎቹ ይዘት እና መንፈስ መገንዘብ እንደሚቻለው አንድ የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት ለማግኘት ማሟለት ያለበት መስፈርቶች መሠረታዊ የሕግ ስህተት መኖር ፤ ውሳኔው የመጨረሻ መሆኑ፤ የመጨረሻው ውሳኔ በሕጉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለሰበር ሰሚ ችሎቱ መቅረቡ ፤ ክርክሩ የፍትሐ ብሔር ጉዳይ ሲሆን የዳኝነት ክፍያ የተፈፀመበት መሆኑ አለያም በደሃ ደንብ የተከፈተ መሆን ይኖበታል፡፡ አንድ ጉዳይ በሰበር ለመታየት ብቁ ለመሆን በመጀመሪያ ጉዳዩ በመደበኛ ፍርድ ቤቶች ወይንም ሌሎች የዳኝነት ሥልጣን በሕግ በተሰጣቸው አካላት ዘንድ የመጨረሻ ፍርድ ያገኘ መሆን አለበት፡፡ አቤቱታ አቅራቢው የይግባኝ ደረጃውን ሳይጨርስ ወይንም ውሳኔውን ለማሳረም የሚችልበት ዕድል እያለው ለሰበር ችሎት አቤቱታ የማቅረብ መብት አይኖረውም፡፡ ውሳኔው ከሰበር ሰሚ ችሎቱ በመለስ ባሉት መደበኛ ፍርድ ቤቶች ወይንም በሕግ የዳኝነት ሥልጣን በተሰጣቸው አካላት ታይቶ በፍሬ ነገሩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ መሆን አለበት፡፡

በተያዘው ጉዳይ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 97 መሠረት በተሰጠው የግብርና ታክስ ሥልጣን መሠረት አድርጎ ያወጣውን የክልሉን የታክስ አስተዳደር ሕግ አዋጅ ቁጥር 241/2008 አንቀጽ 131/1 እና 119/1 ሥር የተመለከተውን በመተላለፍ ሚያዝያ 6 ቀን 2014 ዓ.ም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ከቀኑ በግምት 5:50 ሰዓት ደርብ አበጀና አፀደ ከተማው የተባሉ ደንበኞች አንድ በየአይነቱ ምግብ እና አንድ ሊትር የታሸገ ውሃ ተጠቅመው ደርብ አበጀ የተባሉት ግለሰብ ለተሰጣቸው አገልግሎት ለከፈሉት 135.00 ብር (አንድ መቶ ሰላሳ አምስት) የግብይት ደረሰኝ አልሰጡም በሚል የቀረበን ክስ የደጀን ወረዳ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣኑ አይቶ የሰጠውን ብይን በመቃወም አመልካች ያቀረበውን የይግባኝ አቤቱታ የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረዙ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚው ችሎት የቀረውን የሰበር አቤቱታ ጉዳዩ የፌደራል ስለሆነ ለክልል ሰበር የሚቀርብበት ሥርዓት የለም በሚል ውድቅ ማድረጉን የሥር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

ተጠሪ በክልሉ ግብር ከፋይነት በግብር ከፋይ መለያ ቁጥር 0052005902፤ በንግድ ምዝገባ ቁጥር AM/EG/DEJEN/1/0001230/2010 ተመዝግበው በደጀን ከተማ 01 ቀበሌ በሆቴልና ሉካንዳ ቤት ንግድ ሥራ በደረጃ "ለ" ግብር ከፋይነት የተሰማሩ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ እንዳልሆኑ ፤ በሥራ አስኪያጅነት የሚመሩት ድርጅታቸው የክልሉን የታክስ አስተዳደር ሕግ አዋጅ ቁጥር 241/2008 አንቀጽ 131/1 እና 119/1 ሥር የተመለከተውን በመተላለፍ ሽያጭ ያለደረሰኝ ፈጽሟል በሚል የክልል ሕግን መሠረት አድርጎ በክልሉ ግብር ከፋይነት በተመዘገቡት ተጠሪ ላይ የቀረበን ክስ በየደረጃ ባሉት ጉዳዩን የማየት ሥልጣን በተሰጣቸው የክልሉ ፍርድ ቤቶች ታይቶ የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ ክልላዊ ጉዳይ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪው ችሎት የፌደራል ጉዳይ ነው በሚል አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ ውድቅ ማድረጉ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80 (3/ለ)፤ የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልል ሕገ- መንግስት ለማጽደቅ የወጣው አዋጅ ቁጥር 59/1994 አንቀጽ 67/2(ሀ እና ሐ) ፤ እንዲሁም የተሸሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 281/2014 ቁጥር 24/1(ለ) ድንጋጌዎችን ስለሚጣረስ በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ቁጥር 2/4(ሀ)፤(ለ) እንዲሁም ቁጥር 10/1(ሐ) መሠረት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ቀጣዩ ተወስኗል፡፡

**ውሳኔ**

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር አጣሪው ችሎት በሰበር በመዝገብ ቁጥር 03-118555 ሚያዝያ 24 ቀን 2015 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 9(1/ለ) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ጉዳዩ የክልል ስለሆነ አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት የማየት ሥልጣን አለው በማለት ወስነናል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

3. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር አጣሪው ችሎት በፍርድ የዘጋውን የሰበር መዝገብ ቁጥር 03-118555 በማንቀሳቀስ አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ ተመልክቶ ተገቢ የሆነውን ህጋዊ ውሳኔ እንዲሰጥ መዝገቡ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 9/2 መሠረት መልሰንለታል፡፡

**መዝገቡ ውሳኔ አግኝቶ ስለተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

**መ/ዐ**

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መ/ቁጥር 248810

ቀን 25/04/2017 ዓ/ም

ዳኞች፡- ሽመክት አሰፋ
እንዳሻው አዳነ
አለማየሁ ሹናራ
ዋዚሞ ዋሲራ
ዘውድቱ ታደሰ

አመልካች ፡- አቶ ተገኘ ደምሴ ወንድአፍራሽ - አልቀረቡም

ተጠሪ ፡- ወ/ሮ አየለች ደሳለኝ እንዳሻው - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የንብረት መፋለም ክስን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የሐረሪ ክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.13375 በቀን 18/11/2011 ዓ/ም የሰጠውን ውሳኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት በመ/ቁ. 04927 በቀን 01/04/2012 ዓ/ም የቀረበውን ይግባኝ ቅሬታ ባለመቀበል የሥር ፍርድ ቤትን

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

ውሳኔ በትዕዛዝ በማጽናት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል አመልካች ሰኔ 09 ቀን 2015ዓ/ም በተጻፈ አቤቱታ ቅሬታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ከሥር ፍርድ ቤቶች የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው በሥር ፍርድ ቤት አመልካች ተከሳሽ ተጠሪ ከሳሽ ሆነው ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ በ23/03/2008ዓ/ም ጽፈው ባቀረቡት ክስ አዋሳኞቹ በክሱ የተጠቀሰው የቤት ቁጥር 144 የሆነ በ 2921 ካ.ሜ የመሬት ይዞታ ላይ ያረፈ ሰባት ክፍሎች ያሉት ፎቅ ቤትና ሰርቪስ ቤት ሟች እህታችን በግዥ አግኝተው ሲጠቀሙበት ቆይተው በ1962 ዓ/ም በነበረው የሶማሊያ ጦርነት ወጥተው ስላልተመለሱ ተጠሪ ከወንድሜ ሻምቤል ፈለቀ ደሳለኝ ጋር በመሆን የእህታችንን መጥፋት እና ወራሽነት በ1972 ዓ/ም አሳውጀውን ቤቱ በውርስ ለተጠሪ እና ወንድሜ ከተላለፈ በኃላ፣ የተጠሪ ወንድም በ1988 ዓ/ም በውርስ ያገኙትን የአከራካሪውን ቤት ድርሻ በስጦታ ያስተላለፉልኝን ጨምሮ ከጠቅላላ ይዞታ ውስጥ በ1394 ካ/ሜ ላይ ካርታ በስሜ 11/09/1996 ዓ/ም የተሰራልኝ ሲሆን ቀሪው 1527 ካ/ሜ ይዞታ እና ፎቅ ቤት ወደ ፊት ይሰራልሻል ተብዬ ነበር፣ከዚያ በኂላ ሟች እህቴ ያከራዩቻቸው የተከሳሽ ቤተሰቦችከ1969 ዓ/ም ጀምሮ በቤት ውስጥ መኖር ቀጠሉ፣ አመልካች ምንም መብት ሳይኖረው በምዕራብ አቅጣጫ የሚገኙትን አምስት ክፍል ቤቶችን ይዞ በማከራየት፣ ከ2001 ዓ/ም እስከ 2004 ዓ/ም ተለጣፊ ቤቶችን በመስራት እየተጠቀሙ በመሆኑና ቤቱንም ለማስረከብ ፈቃደኛ ስላልሆኑ በሕገ-ወጥ መንገድ የሠሩትን ቤት አፍርሰው የቤት ቁጥር 144 እና ይዞታውን ለቀው እንዲያስረክቡ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁኑ አመልካች ሥር ፍርድ ቤት ባቀረበው መልስ አዋጅ ቁጥር 47/67 ከመውጣቱ በፊት አከራካሪው ቤት በወ/ሮ የሺ ደሣለኝ ስም የተመዘገበ ቢሆንም በመንግስት ተወርሶ የአመልካች ወላጅ እናት ወ/ሮ አሰለፈች አስፋው በስማቸው የነበረውን በአሰበ ተፈሪ ቀበሌ 02 የነበራቸውን 4 (አራት) ክፍል ደጃፍ ቤት ለመንግስት አስረክበው አሁን ለክሱ ምክንያት የሆነውን የቤት ቁጥር 144 በለውጥ አግኝተው በአመልካች እና በወላጆቻቸው እጅ የቆየ መሆኑ እየታወቀ የተጠሪ አውራሽ በሕይወት እያሉ ያልጠየቁትንና አዋጅ ቁጥር 47/67 በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተሰጠውን ካርታ መነሻ እንዲሁም ቤቱ የውርስ ንብረት መሆኑን ሳረጋግጡ በ1972 ዓ/ም የያዙትን የወራሽነት ማስረጃ በመያዝ ብቻ አውራሻቸው በሕይወት አያሉ ባለየጠቁት እንዲሁም በሥጦታ ከወንድሜ አገኘሁ የሚሉትም የማይጸና ስለሆነ የቀረበው ክስ የሕግ ድጋፍ የለውም ተብሎ ውድቅ እንዲሆን ተከራክረዋል፡፡

የጀንኤላ ቀበሌ አስተዳደር ወደ ክርክሩ እንዲገባ ታዞ ወደ ክርክሩ በመግባት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የፍሬ ነገር ቤቱ በመንግስት የተወረሰ እና በቀበሌ እጅ ያለ ቢሆንም ከማህደር ማስረጃ መጥፋቱን በመግለጽ ተከራክሯል፡፡

የሐረሪ ክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመስማት እንዲሁም የቤቱን ማኅደር አስቀርቦ ከመረመረ በኂላ በሰጠው ውሳኔ ቤቱ እና ቦታውን ሟች የተጠሪ እህት1962 ዓ/ም በግዥ ያገኙችው መሆኑን፣ በስሟም ግብር ይከፈልበት እንደነበር ፣ከጊዜ በኃላ በተጠሪ ስም ግብር ሲከፈል እንደነበር፣ የአመልካች ወላጅ እናት ወ/ሮ አሰለፈች አስፋው በአሰበ ተፈሪ ከተማ የነበራቸውን ቤት ለመንግስት

አስረክበው የቤት ቁጥር 144 በአማራጭ የተሰጣቸው ለመሆኑ ማስረጃ ማህደር ውስጥ አለመገኘቱን ፤የቀበሌው መግለጫ አንደ በ1992 ዓ/ም የቤት ቁጥር 144 ተወርሷል የሚል ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ በ1996 ዓ/ም ሟች የሺ ደሳለኝ (የተጠሪ እህት) በግዥ ያገኙት እና በስማቸው ግብር እንደተከፈለ የሚገልጽ እርስ በርስ የሚቃረን ማስረጃ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፤ የቤቱ ማኅደር ሟች የሺ ደሳለኝ (የተጠሪ እህት) በ1962 ዓ/ም በግዥ ያገኘችው፤ካርታ የነበረው፤ ግብር የሚከፈልበት ሆኖ ከይዞታው ላይም በ845 ካ.ሜ ላይ ያረፉ አምስት ክፍል ቤቶችን ለአቶ ዴቅ ፈራህ መሸጧን የቤቱ ማኅደር ያመለክታል፡፡ ስለሆነም ቤቱ የሟች የሺ ደሳለኝ መሆኑ ስለተረጋገጠ አመልካችም ሆነ የቀበሌ አስተዳደሩ የያዙትን ቤት ለአቶ ዴቅ ፈራህ ከተሸጠው 845 ካ/ሜ ውጭ የሟች እህቷን ወራሽነት ላረጋገጠችው ለተጠሪ እንዲያስረክቡ እና የቀበሌ ነው ተብሎ በሳይት ፕላን የተጠቀሰውም እንዲሰረዝ በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች እና የቀበሌ አስተዳደሩ ይህን ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ችሎት አቅርበው ፍ/ቤቱ በመ/ቁ 04927 በቀን 01/04/2012 ዓ/ም የይግባኝ ቅሬታውን በመሰረዙ በመቀጠል ቅሬታውን በየበኩላቸው ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍ/ቤቱ አጣምሮ መርምሮ አመልካች ያቀረበውን አቤቱታ ባለመቀበል ሰርዟል፡፡

አመልካች አሁንም ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ችሎቱም በሰ/መ/ቁጥር 227437 የካቲት 28 ቀን 2015 ዓ/ም በዋለው ችሎት አመልካች አሜሪካዊ ዜጋ ስለሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለውም በማለት ትዕዛዙን ሰርዞ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ችሎት በሰጠው ውሳኔ ላይ አቤቱታ የማቅረብ መብትን በመጠበቅ በአብላጫ ድምጽ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ መሰረት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት በመ/ቁ. 04927 በቀን 01/04/2012 ዓ/ም የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች በ09/10/2015 ዓ/ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን ይዘቱም፡- ከ1967 ጀምሮ በተጠሪ እጅ ገብቶ ስለማያውቅ ክስ በይርጋ ቀሪ ነው እንዲሁም ተጠሪ አከራይቶ ሳይሆን ቀበሌ ሰጥቶኝ ከ45 ዓመት በላይ የምኖርበት ስለሆነ ተጠሪ ክስ ለመመስረት የሚያበቃት መብትና ጥቅም የላትም በሚል ያቀረብነው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ መወሰኑ ስህተት ነው፡፡ አከራካሪው ቤትበአዋጅ ቁ.47/67 መሠረት በ1967 ዓ/ም በምትክነት ለአመልካች ቤተሰቦች በእናቴ ስም የተሰጠ ስለመሆኑና የቤት ቁጥር 144 በ1967 ዓ/ም በትርፍነት ተመዝግቦ ኪራይ ቀመስ እና የተወረሰባቸው ቤት ስለመሆኑ በቂ የሰነድ ማስረጃዎች ለሥር ፍ/ቤት ቀርቦ እያለ ፍትሐዊ ባልሆነ ሁኔታ የተጠሪን ማስረጃ ብቻ መሰረት አድርጎ መወሰኑ ስህተት ነው፡፡ የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት የይዞታ ማረጋገጫን የመሰረዝ ስልጣን ሳይኖረው ይሰረዝ ብሎ ውሳኔ መስጠቱ ሊታረም የሚገባው መሰረታዊ ስህተት ነው፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲሻር እና ወጪ እና ኪሳራተጠሪ እነዲከፍሉ እንዲወሰኝልን የሚል ነው፡፡

ሰበር ችሎትም ጉዳዩን መርምሮ ለክርክር መነሻ የሆነው የመኖሪያ ቤት ከአዋጅ ቁጥር 47/67 በፊትም ሆነ በኋላ በተጠሪ እጅ መግባቱ ባልተረጋገጠበትና ቤቱ በአመልካች እጅ የቆየና አመልካች ሲጠቀምበት የነበረ መሆኑ ተመልክቶ ባለበት፣ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች አከራካሪው ቤት በመንግስት የተወረሰ ነው እናቴ ቤቷን ለመንግስት ሰጥታ ይህንን ቤት በለውጥ ይዛ በወላጆቼና በአመልካች እጅ የቆየ ነው በማለት ያቀረበውን ክርክር ውድቅ በማድረግ ቤቱ የተጠሪ እህት በግዢ ያገኘች በመሆኑና በመንግስት መወረሱ አልተረጋገጠም በሚል ምክንያት አመልካች ቤቱን ለቀው ለተጠሪ እንዲያስረክቡ በማለት የወሰኑበትን አግባብ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 45161፣ 48699 እና የፌደሬሽን ምክር ቤት በ5ኛ የፓርላማ ዘመን 4ኛ አመት መስከረም 29 ቀን 2011ዓ/ም ከሰጠው አስገዳጅ  ውሳኔ አንጻር ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በበኩላቸው በ08/11/2016 ዓ/ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ጥንታዊ ፎቅ በአጠቃላይ 7(ሰባት) ክፍሎች ያሉት ሲሆን ከእነዚህ ክፍሎች ውስጥ በመንግስት የተወረሱና ቀበሌ ኪራይ የሚቀበልባቸው 3 ክፍሎች ብቻ ሲሆኑ ቀሪው የፎቁ ክፍል በተጠሪ እጅ እና ቁጥጥር ሥር ሆኖ የአመልካች ወላጆች እስከእለተሞታቸው ድረስ የኖሩበት ከሞቱ በኋላ በሌሎች እጅ የገባ እንጂ በአመልካች እጅ አልቆየም፣ የአመልካች ወላጆችም በዚህ ቤት ውስጥ ሊገቡ የቻሉት የቤቱ ባለቤት የሆኑት የተጠሪ እህት ከመሞታቸው በፊት አከራይተዋቸው ስለነበረ እንጂ ከመንግስት ተከራይተውት የነበረ ባለመሆኑ በሰበር ችሎቱ የተጠቀሰው የሰበር ውሳኔ እና የፌደሬሽን ምክር ቤት ውሳኔ ለጉዳዩ አግባብነት የለውም፡፡ ተጠሪ ያቀረብኩት ክስ የመፋለም ክስ በመሆኑ በይርጋ አይታገድም፡፡ የቤት ቁጥር 144 ስለመወረሱ የሚያስረዳ ማስረጃ ቅጽ 003 ወይም ሌላ ተመሳሳይ ውጤት ያለው ሰነድ አለመኖሩ የቤቱ ማህደር ቀርቦ እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ዐ/ሕግ ወደ ክርክሩ ገብቶ ቤቱ ስለመወረሱ እንዲያስረዱ እድል ተሰጥቶ ስለመወረሱ የሚያስረዳ ማስረጃ ባለመገኘቱ የተሰጠ ውሳኔ እንጂ አመልካች እንዳሉት የተጠሪን ማስረጃ ብቻ መሰረት ተደርጎ የተሰጠ ውሳኔ የለም፡፡ በመሆኑም በውሳኔው ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም ተብሎ ሊጸና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በመልስ መልሱ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን አቤቱታና መልስ ለጉዳዩ ከተያዘው ጭብጥ ከሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች አንፃር መርምረነዋል፡፡

እንደመረመርነውም አከራካሪ የሆነውይዞታ አጠቃላይ 2921 ካ/ሜ ሆኖ 1962 ዓ/ም በሟች የሺ ደሳለኝ የተመዘገበ ሲሆን  ከዚህ ውስጥ 1394 ካ/ሜ በ1996 በተተሪ ስም ሲመዘገብ ቀሪው 1527 ካ/ሜ ቦታ እና በላዩ ላይ ያለው የቤት ቁጥሩ 144 የሆነው ፎቅ ቤት ከ1962 ጀምሮ በተጠሪ እጅ ያልገባ መሆኑና ቅጹ ከማህደር ውስጥ የጠፋ ቢሆንም ይህ ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/67 በመንግሥት ተወርሶ አሰበ ተፈሪ የነበረ የአመልካች እናት ቤት መንግሥት በውርስ በመውሰድ በምትክነት የሰጣቸው ስለመሆኑ እና ከተሰጠበት

ከ1967 ዓ/ም ጀምሮ አመልካች እና ቤተቦቹ እየኖሩበት ያሉ ስለመሆናቸው የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ግልባጭ ያስረዱናል፡፡

አዋጅ ቁጥር 47/67 በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተሰጠን ካርታ መሠረት በማድረግ ክስ ለመመስረት የሚያስችል መብት ወይም ጥቅም የሌለ ስለመሆኑ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 48699 አስገዳጂ የሕግ ትርጉም ተሰትቶበታል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

የፌዴሬሽን ምክር ቤት በ4ኛ ዓመት 1ኛ መደበኛ ጉባኤ በቀን 29/01/2011 ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ በሰጠው ውሳኔ በአገር አቀፍ ደረጃ ከአዋጅ ውጭ በመንግሥት የተያዙ ቤቶችን አስመልክቶ ወደ ባለንብረቶቹ ለመመለስ ኤጀንሲ የተቋቋመ መሆኑን፣ ከአዋጅ 47/67 ውጭ ቤት ተወስዶብኛል የሚል ሰው ቤቱ የተፈቀደለት ከሆነ ወይም ፕራይቬታይዜሽን ኤጄንሲ ቤቱ እንዲመለስለት ካልተወሰነ በስተቀር ለረዥም ጊዜ በመንግሥት ቁጥጥር ስር ሆኖ ሲተዳደር የነበረ ንብረት ለአመልካች እንዲመለስ መወሰን ከጊዜ ርዝመት ጋር ተያይዞ ተአማኒነት የሌለው ማስረጃ እንዲቀርብ የሚያበረታታ በመሆኑ እንዲህ ዓይነት ቤቶች የመንግሥት እንደሆኑ ይቆጠራሉ ሲል ወስኗል፡፡

እንዲሁም የፌደሬሽን ምክር ቤትም በ6ኛ የፓርላማ ዘመን 3ኛ አመት 1ኛ መደበኛ ጉባኤ በመ/ቁ/108/15 መስከረም 29 ቀን 2016 ዓ/ም ከላይ በተመለከተው በምክር ቤቱ ውሳኔ መሰረት ከዛሬ 40 ዓመት በፊት በመንግስት እጅ የገባን ቤት በሚመለከት ቅፅ ካልቀረበ ቤቱ በመንግስት አንደተወረሰ አይቆጠርም የሚለው ከቅፁ ዓላማ እና ቆይታ አንፃር በምክር ቤቱ ውሳኔ መሰረት ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ በተጨማሪም ተጠሪ የቤቱ ባለሀብት መሆናቸውን የሚያሳይ ካርታ አለኝ በማለት ያቀረቡትም ካርታው የተሰጠው ከአዋጅ 47/67 በፊት በመሆኑ በፍ/ህግ አንቀፅ 1195 መሰረት ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ አከራካሪው ቤትም በመንግሥት ቁጥጥር ስር ሆኖ እየተዳደረ የሚገኝ ስለሆነና ተጠሪ ከአዋጅ ውጭ የተያዙ ቤቶች እያጣራ እንዲመልስ ስልጣን ወደ ተሰጠው የፕራይቬታይዜሺን ኤጀንሲ ጉያቸውን አቅርበው ቤቱ እንዲመለስላቸው ያልተወሰነላቸው በመሆኑ፣ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ለረዥም ጊዜ በመንግሥት ቁጥጥር ስር የነበሩ ቤቶች አጣ ፈንታ አስመልክቶ ከሰጠው ውሳኔ አንጻር የፍ/ቤቱ ውሳኔ ከምክር ቤቱ ውሳኔ እና ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 37 (1) ጋር የሚቃረን ስለሆነ እነዲህ አይነት ቤቶች የመንግሥት እንደሆነ ይቆጠራሉ ሲል ወስኗል፡፡

አሁን ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ በ1527 ካ/ሜ ቦታ እና በላዩ ያለው የቤት ቁጥሩ 144 የሆነው ፎቅ ቤት እና አያይዞ አመልካች የሠራቸውን ሰርቢስ ክፍሎች በተመለከተ ክስ ያቀረቡት ከአዋጅ 47/67 በፊት በ1962 ለአውራሽዋ ለሚች የሺ ደሳለኝ የተሰጠውን ካርታ መሠረት በመስድረግ በመሆኑ፣ እንዲሁም ከ1962 ዓ/ም ሆነ ከ1967 ዓ/ም ጀምሮ በመንግስት በሚተዳደር ቤት ላይ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በ4ኛ ዓመት 1ኛ መደበኛ ጉባኤ በቀን 29/01/2011 ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ሆነ በ6ኛ የፓርላማ ዘመን 3ኛ አመት 1ኛ መደበኛ ጉባኤ በመ/ቁ/108/15 መስከረም 29 ቀን 2016 ዓ/ም ባደረገው ስብሰባ የተሰጡ ውሳኔዎችን የሚቃረን በመሆኑ በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሀ) እና አንቀጽ 10(1/ሀ) አንጻር መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የሐረሪ ክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.13375 በቀን 18/11/2011 ዓ/ም የሰጠውን ውሳኔ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት በመ/ቁ. 04927 በቀን 01/04/2012 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1/ለ) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በ1527 ካ/ሜ ይዞታ ላይ ያለውን የቤት ቁጥሩ 144 የሆነው ፎቅ ቤት እና አያይዞ አመልካች የሠራቸውን ሰርብስ ክፍሎችን አመልካች ለተጠሪ ሊለቅ አይገባም ብለናል፡፡
3. በዚህ መዝገብ ሰኔ 26 ቀን 2016 ዓ/ም የተሰጠ እግድ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡
4. የዚህ ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡
5. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላልፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

**<u>ማስታወሻ</u>፡** - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ249348

ቀን28/4/2017

የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ውዝፍ ችሎት

ዳኞች1. ሺመክት አሰፋ

2. እንዳሻው አዳነ

3 .አለማየሁ ሹናራ

4.ዋዚሙ ዋሴራ

5 .ዘውዲቱ ታደሰ

አመልካች(ቾች) አቶ ጌታቸው ጎነሞ - ጠበቃ ወ/ሮ ምትዬ መዝገቡ - ቀረቡ

ተጠሪ(ዎች) አቶ ፍሰሀ ታምራት - ከጠበቃ ትንሳኤ ሽዋለም ጋር ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ክርክሩ የጀመረው በሆሳእና ከተማ መጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው። የአሁን ተጠሪ ከሳሽ የነበሩ ሲሆን አመልካች ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ። ክሱ ሪል እስቴት ለመስራት ከከተማው ከተረከብኩት ቦታ ውስጥ ከእጣ ቁጥር 29 እስከ 34 ድረስ ያሉትን ስድስት ቦታዎች አመልካች እኔ ታምሜ ለህክምና አዲስ አበባ በሄድኩበት 2007 አ.ም አጥረው ስለያዙብኝ ይለቀቁልኝ የሚል ነው።በአመልካች በኩል ከፍተኛ ገንዘብ አውጥቼ የግንብ አጥር ያጠርኩት ተጠሪ በሌሉበት አደለም ፤እንደውም ፈቅደውና ባሉበት ነው፤ ባለቤቱ ሳይቃወም በሰው መሬት ላይ ህንጻ የሰራ ሰው የህንጻው ባለቤት እንደሚሆን በፍ/ህ/ቁ 1179 ከመደንገጉ በላይ ይህን የሚደግፍ በሰ/መ/ቁ105125 የተሰጠ የሰበር ውሳኔም ስላለ ክሱ ውድቅ ይደረግልኝ ብለው ተከራከሩ።

የመጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤቱ የአመልካችን ክርክር ውድቅ በማረግ ቦታውን ለቀው እንዲወጡ ወሰነ።በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር ተሰኝተው ለሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርበው ፤ ፍርድ ቤቱ አመልካች የሰሩት ተጠሪ ሳይቃወሙ ነው በማለት የመጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤቱን ውሳኔ በመሻር ለአመልካች ወሰነ። ተጠሪ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቅሬታ ቢያቀርቡም የከፍተኛውን ፍርድ ቤትን ውሳኔ አጸና።ተጠሪ ለደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርበው የሰበር ችሎቱ የከፍተኛና ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎቶችን ውሳኔ በመሻር የመጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ ትክክል ነው በማለት ለተጠሪ ወስኗል። ይህ የሰበር ቅሬታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው።

የቅሬታው ዋና ነጥብ የሚያጠነጥነው ተጠሪ ሳይቃወሙኝ በመሬታቸው ላይ ህንጻ የገነባሁ በመሆኑ፤ የክልሉ ሰበር ችሎት የፍ/ህ/ቁ 1179፣ የሰበር /መ/ቁ105125 እና የህንጻ አዋጅ ቁጥር 624/2001 አንቀጽ 2(2) ን በሚጋጭ መልኩ በመወሰን መሰረታዊ የህግ ስህተት የፈጸመ ስለሆነ ይሻርልኝ የሚል ነው።በዚህ መዝገብ ከሰበር መዝገብ ቁጥር 105125 እና ከህንጻ አዋጅ ቁጥር 624/2001 አንቀጽ 2(2) አንጻር የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት መኖር ያለመኖሩን ለማጣራት መዝገቡ ያስቀርባል ተብሎ ግራቀኙ መልስና የመልስ መልስ ተቀባብለዋል። እኛም የቀረበውን ክርክር፣የተያዘውን ጭብጥ፣ የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ እና ህጉን በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል።

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

የፍትሀብሄር ህግ ቁጥር 1179 ባለቤቱ ሳይቃወም በሰው መሬት ላይ ህንጻ የገነባ ሰው የህንጻው ባለቤት ይሆናል ይላል፡፡ የህንጻ አዋጅ ቁጥር 624/2001 አንቀጽ 2(2) ደግሞ ህንጻ የሚለውን ሲተረጉም ለመኖርያ፣ለቢሮ፣ለፋብሪካ ወይም ለማናቸውም ሌላ አገልግሎት የሚውል ቋሚ ወይም ጊዜያዊ ግንባታ ነው ይላል፡፡ የሰበር መዝገብ ቁጥር 105125 ላይ በተሰጠው ውሳኔ ባለቤቱ ሳይቃወም በሰው መሬት ላይ ንብረት ያፈራ ሰው የንብረቱ ባለቤት ነው ይላል፡፡ አመልካች የሰሩት አጥር ነው፡፡ ህንጻ በአዋጅ በተሰጠው ትርጉም መሰረት አመልካች የሰሩት አጥር ህንጻ ሊባል ይችላልወይ የሚለውን እንመልከት፡፡ ህንጻ ለመኖርያ፣ ለቢሮ ፣ለፋብሪካ ወይም ለማናቸውም ሌላ አገልግሎት የሚውል ቋሚ ወይም ጊዜያዊ ግንባታ ነው፡፡ ለመኖርያ፣

ለቢሮ፣ለፋብሪካ የተባሉት ሁሉም ቤቶችና የቤት ቅርጽ ያላቸው ናቸው፡፡ከዚህ በኋላ ለማናቸውም አገልግሎት የሚባለውም እንዲሁ የቤት ቅርጽ ያለው ሆኖ ለመጋዘን ለንግድ የመሳሰለ ከሚካተት በስተቀር አጥርን በዚህ ውስጥ ማካተት ተገቢ የሆነ ትርጉም ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሰበር መዝገብ ቁጥር 105125 ባለቤቱ ሳይቃወም በሰው መሬት ላይ ንብረት ያሰፈረ የንብረቱ ባለቤት ይሆናል ተብሎ የተወሰነው አጥርን ለማካተት ነወይ የሚለውን እንመልከት፡፡ እንዲሁ ላይላዩን ሲታይ የሚያካትት ይመስላል፡፡ ጠለቅ ብለን ስናየው ግን ውሳኔው የተመሰረተው ባለቤቱ ሳይቃወም በሰው መሬት ላይ ህንጻ የሰራ ሰው የህንጻው ባለቤት ይሆናል በሚለው የፍ/ህ/ቁ 1179 ነው፡፡ ህንጻ ምን ማለት እንደሆነ ደግሞ የህንጻ አዋጅ ሲደነግግ አጥርን ባካተተ መልኩ የደነገገ አደለም፡፡ በዋናነት ደግሞ የሰበር መዝገብ ቁጥር 105125 ላይ ውሳኔ የተሰጠው ቤት በሌላ ሰው መሬት ላይ ከመሰራት ጋር የተያያዘ ክርክር ተነስቶ እንጂ አጥርና መሰል ሌላ ንብረት በሌላ ሰው መሬት ላይ ከመኖር ጋር የተያያዘ ክርክር ተነስቶ አደለም፡፡ በመሆኑም የክልሉ ሰበር ችሎት የፈጸመው ምንም መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሌለ ከዚህ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

- የደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ21543 በሚያዝያ 5/2015 የሰጠው ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሌለ በሰበር/ስ/ስ/መመርያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1)(ሀ) መሰረት አጽንተነዋል፡፡
- በዚህ መዝገብ ሀምሌ17/2015 ተሰጠው እግድ ተነስቷል፡፡

- የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ ይቻቻሉ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መዝገብ ቁጥር 249911

ታህሳስ 24 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች፡-ሽመክት አሰፋ

እንደሻው አዳነ

አለማየሁ ሹናራ

ዋዚሞ ዋሲራ

ዘዉዲቱ ታደሰ

አመልካች፡-ወ/ሮ ኀበኔ ጉዬ - ቀረቡ

ተጠሪ፡-አቶ ሁሴን ሶራ - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

ፍርድ

ጉዳዩ የንብረት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በሻሸመኔ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ሲጀምር ተጠሪ ከሳሽ ፣አመልካች 2ኛ ተከሳሽ፣ አሁን የክርክሩ አካል ያልሆነው ጀማል ከድር 1ኛ ተከሳሽ ሆነው ተከራክረዋል፡፡

የሰበር አቤቱታለዚህ ችሎት የቀረበው የሻሸመኔ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/14689 በቀን25/01/2015 ዓም የሰጠውን ውሳኔ የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 45377 በቀን 15/02/2015 ዓ/ም ቅሬታውን ባለመቀበል ትዕዛዝ በመስጠቱ፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 407521 በቀን 18/05/2015 ዓ/ም እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ/ 421547 በቀን 24/08/2015 ዓ/ም የሥር ፍረድ ቤቶች ውሳኔ በማጽናት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

የሰጡትን ውሰኔ በመቃወም አመልካች ሰኔ 27 ቀን 2015 ዓ/ም የተጻፈ ቅሬታ በማቅረባቸው ነው፡፤

ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት ያቀረቡት ባቀረቡት ክስ ተጠሪ (2ኛ ተከሳሽ) በሻሸመኔ ከተማ በዳዲ ቦቄ ቀበሌ ውስጥ ያለውንና በቀን 22/11/2011 ዓም በተደረገ የግዥ እና ሽያጭ ውል ከአቶ አሊዩ ኡሱከተባለው ሰው  በግዢ ያገኘሁትን 360 ካ/ሜ ላይ ያረፈ ቤቴን በአደራ የዚህ መዝገብ አካል ላልሆነው የሥር 1ኛ ተከሳሽ ጀማል ከዲር ኪራይ እየሰበሰበ እንዲጠብቅልኝ በእምነት ሰጥቸው ወደ ውጭ ሀገር ሄጄ ስመለስ ተከራዮችን በማስወጣት አመልካችን በቤቱ ውስጥ ያስገባ በመሆኑ 2ኛ ተከሳሽ እንዲትለቅ ስጠይቃት የሰጠሽውን ሰው ጠይቅ ያለችኝ ስለሆነ እና 1ኛ ተከሳሽም ከቤት አስወጥቶ እንዲያስረክበኝ ብጠይቀውም ፈቃደኛ ባለመሆኑ ተከሳሾች ቤቱን ለቀው እንዲወጡልኝ እና ወጪ እና ኪሳራ እንዲወሰን የሚል ነው፡፡

1ኛ ተከሳሽ መጥሪያ ደርሶት ራሱም ያልቀረበ እና መልስም ያላቀረበ ስለሆነ የታለፈ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያሳያል፡፡ 2ኛ ተከሳሽ (አመልካች) መቃወሚያ አቅርበው በፍ/ቤቱ ውድቅ የተደረገ ሲሆን አከራካሪውን ቤት ተጠሪ ለሥር 1ኛ ተከሳሽ በቀን 28/11/2011 ዓ/ም ሽጠውላቸው እና ከ1ኛ ተከሳሽ በቀን 21/02/2013 ዓ/ም ገዝቼ ተጨማሪ ግንባታ በመስራት የምኖርበት በመሆኑ ክሱ ውድቅ ሆኖ የሞራል ካሣ እና ወጭና ኪሳራ ይወሰንልኝ በማለት በአማራጭ ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የሻሸመኔ ወረዳ ፍ/ቤትም ጉዳዩን መርምሮ ግንቦት 03 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት አመልካች ለከሳሽ እንዲትለቅ እና የገዛችበት ገንዘብ ከ1ኛ ተከሳሽ የመጠየቅ መብቷን ጠብቆ የሰጠውን ውሳኔ የኦሮምያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመሻር ጭብጥ ይዞ በመመለሱ  ወረዳ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ዳግም መርምሮ አመልካች (2ኛ ተከሳሽ ) ቤቱን መልቀቅ የለባትም፤ ነገር ግን ከሳሽ  ቤቱ የተሸበት ዋጋ 1ኛ ተከሳሽን የመጠየቅ መብት አለው በማለት በቀን 28/06/2014 ዓ/ም ውሳኔ ያሳለፈ ሲሆን የኦሮምያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በድጋሚ ቤቱ የሚገኘው በከተማ ወይም በገጠር ክልል መሆኑን፣ከዚህ ፊት የማን እነደነበረ ፣ ከተከራካሪዎቹ የማን እንደሆነ እና እነደት እንዳገኙ፣ከሚመለከተው አካል በማጣራት ቀድሞ ከተሰሙት ምስክሮች ጋር መርምሮ እንዲወስን በነጥብ መልሶታል፡፡  ለሁለተኛ ጊዜ በነጥብ የተመለሰለት የሥር ወረዳ ፍርድ ቤትም 1ኛ ተከሳሽ ከተጠሪ ቤቱን ሳይገዙ በሀሰት ተመሳስሎ በተሰራ ሰነድ ለአመከልካች ቤቱን ያስተላለፉ መሆኑን፣ አመልካችም ተገቢውን ማጣራት ሳያደርጉ የማይንቀሳቀስ ንብረት ግዢ ያደረጉ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጧል በሚል  የቅን ልቦና ገዢ ናቸው ሊባል አይቻልም

በማለት የሥር 2ኛ ተከሳሽ (አመልካች) ቤቱን ለቀው ለተጠሪ እንዲያስረክቡ እና የቤቱን ዋጋ ከሥር 1ኛ ተከሳሽ እንዲትጠይቅ በመ/ቁ 14689 መስከረም 25 ቀን 2015 ዓ/ም ፍርድ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በውሳኔው ቅር ተሰኝተው ለምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ፣ለኦሮምያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎቶች እና ለኦሮምያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቶቹ በየደረጃው የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበው የህንን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወት ነው፡፡ በቅሬታቸውም የተጠሪ አድራሻ ሳዑዲ አረቢያ መሆኑን ከክሱ መረዳት የሚቻል ሲሆን የውጭ ሀገር ዜጋን በሚመለከት የሚቀርብ ክስ እና አከራካሪው ይዞታ በሌላ ቀበሌ ሥር የሚገኝ የገጠር መሬትን የሚመለከት በመሆኑ የስር መጀመርያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም፡፡አመልካች ቤቱን በግዥ በብር 500,000 /በአምስት መቶ ሺህ ብር/ ያገኘሁ ስለመሆኑ በተሻለ ማስረጃ በስር ፍ/ቤት አረጋግጬ እያለሁ የቀረበው ክስ ሆነ ተብሎ የቤት ዋጋ በመጨመሩ ያላግባብ ለመበልጸግ በማሰብ የቀረበ ክስ ነው፡፡ ቤቱን ተገቢ ማጣራት በማድረግ ገዝቼ በቀበሌ ያስመዘገብኩ ስለመሆኑ፣ በቤቱ ምክንያት የቀበሌ ነዋሪነት መታወቂያ በማግኘት የተለያዩ ክፍያዎችን የፈጸምኩ በመሆኑ እንዲሁም ተጠሪ ቤቱን በሚመለከተው አካል በማይንቀሳቀስ መዝገብ ያልተመዘገበ እና ሻጭ ከእነ ሚስቱ በማስጠራት የፈጸምኩት ውል መሆኑ ቤቱን በህጋዊ መንገድ ስለመግዛቴ አስረጂ ሁኖ እያለ የስር ፍ/ቤት በተቃራኒው የሰጠው ውሳኔ ተሽሮ እንዲወሰን በማለት ጠይቀዋል፡፡

የሰበር ችሎት መዝገቡን መርምሮ ለክርክሩ መነሻ ሆነው ቤት እና ይዞታ በሚመለከተው አካል የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የነበረው መሆኑ ባልተረጋገጠበት ግራ ቀኙ ያቀረቡትን የቤት ሽያጭ ውል በሚመለከተው አካል ፊት የተደረገ እና የተመዘገበ መሆኑ ባልተመለከተበት አመልካች ይህን ቤት እና ይዞታ ስትገዛው ከአንድ ጠንቃቃ ገዢ የሚጠበቀውን ጥንቃቄ ስላላደረገች የቅን ልቦና ገዢ አይደለችም በማለት ቤቱን ለተጠሪ ለቃ እንድታስረክብ በስር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን በኢፌድሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40 እና ይህ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 60720፣88084(የታተመ)፣ 163964 (ያልታተመ) እና በሌሎች መዛግብት ላይ ስለቅን ልቦና ገዢ ጋር በተያያዘ ከሰጠው የህግ ትርጉም አንጻር ለመመርመር ሲባል ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል ፡፡

ተጠሪ በበኩላቸው ባቀረቡት መልስ አመልካች ቤቱን ገዝቻለሁ በማለት የፈጸሙት ውል ላይ የሚገኝ የቤቱ አድራሻ እና ትክክለኛ የቤቱ አድራሻ መለያየቱ እና የስር 1ኛ ተከሳሽ ከአመልካች

ጋር ውል አለመፈረማቸውን ማመናቸው አመልካች ውሉን ከቅን ልቦና ውጪ የተዋዋሉት ስለመሆኑ አስረጂ ነው፡፡አመልካች ቤቱን ሲትገዛ የስር 1ኛ ተከሳሽ ከተጠሪ ጋር አድርገዋል የተባለውን ውል ህጋዊነት ሳታረጋግጥ እና ባለቤቱን ያላቀረበበትን ምክንያት ሳትመረምር እንዲሁም በሚመለከተው አካል ፊት ባልተደረገ ውል ከትክክለኛ ባለንብረት ካልሆነ ሰው የገዛችው ስለመሆኑ እና ይህም አመልካች ላይ የመነቀል ውጤት ያለው በመሆኑ የተሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው፡፡አመልካች ቤቱን ገዝታ በቀበሌ ያስመዘገበች ስለመሆኑ ያቀረበችው ክርክር በስር ፍ/ቤት ልተነሳ አዲስ ፍሬ ነገር በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ የሚነቀፍ ስላልሆነ እንዲጸናልኝ ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም አቤቱታቸውነ በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኑን አቤቱታ እና መልስ ከሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ግልባጭ፣ከተያዘው ጭብጥ እና አግባብነት ካቸው የሕግ ድንጋጌዎች አንጻር መዝገቡን መርምሮታል፡፡

አንደመረመርነውም ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት እና ይዞታ ተጠሪ ከአቶ አልዩ ኡሱ በመንደር ውል በግዥ አግኝቶ የሥር 1ኛ ተከሳሽ ለነበረው በአደራ ሰጥቶት 1ኛ ተከሳሽ ደግሞ ከተጠሪ እንደገዛ አድረጎ ለአመልካች በተመሳሳይ ሁኔታ የሸጠ መሆኑ እና የግራ ቀኙም የግዥ ውል በሚመለከተው አካል ያልተመዘገበ መሆኑ፣በሀሰተኛ ሰነድ እና በእምነት ማጉደል ወንጀል 1ኛ ተከሳሽ ጥፋተኛ ሆኖ የተቀጣ መሆኑ አና ቤቱና እና ይዞታው በአመልካች እጅ የሚገኝ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ በሥር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ እና ድምዳሜ ላይ የተደረሰበት ጉዳይ ነው፡፡

ግራ ቀኙን የሚያቀራክረው እና በዚህ ችሎት አልባት የሚያስፈልገው አከራካሪ ነጥብ በሥር ፍርድ ቤቶች ከተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች አንጻር መልካች የቅን ልቦና ገዥ መሆን አለመሆናቸው ላይ ነው፡፡

በፍ/ሕ/ቁጥር 1195 ድንጋጌ መሠረት የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነትን በማረጋገጥ በአስተዳደር ክፍል የምስክር ወረቀት ሲሰጥ የምስክር ወረቀቱን ያገኘው ሰው የማንቀሳቀስውን ንብረት ባለሀብት ሆኖ ሊገመት እንደሚገባ እና ለሌላ ሰውም ማስተላለፍ የሚችለው ያለውን ሀብቱን ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡በፌ/ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ችሎትም በሰ/መ/ቁ. 163964፣60720 እና ሌሎች መዛግቢት ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

በሌላ በኩል የማይነቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል ውሉን እንዲመዘግብ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል ወይም ተቋም ፊት ካልተደረገ ወይም ካለተመዘገበ የማይጸና ስለመሆኑ እና በሦስተኛ ወገን ላይም መቃወሚያ ሊሆን እንደማይችል በፍ/ሕ/ቁጥር 1723፣1727፣2877 እና 2888 ተደንግጓል፡፡ በፌ/ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ችሎትም በሰ/መ/ቁ. 21448 እና ሌሎች በርካታ መዛግቢት ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡

በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ሕጋዊ መብት የለሌው ሰው በውል ለገዥው መድህን ለመሆን ግዴታ ገብቶ ሽያጩን አከናውኖ ሲገኝም ትክክለኛው ባለሀብት ሊጠይቅ የሚችለው ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጎ የገዛውን ገዥ ሳይሆን ሻጩን ስለመሆኑ ነገር ግን ገዥው በበኩሉ ተገቢውን ጥንቃቄ ሳያደርግ መብት ከለሌው ሰው ገዝቶ ከሆነ ለትክክለኛው ባለሀብት ተጠያቂ እንደሆነ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2882 እስከ 2884 ድረስ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች እንዲሁም ከፍ/ሕ/ቁጥር 997 ድንጋጌ መንፈስ እና ይዘት የምንገነዘበው ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አከራካሪ የሆነው ቤት ከግራ ቀኙ በማናቸውም ያልተመዘገበ መሆኑ እና የግዥ ውላቸውም ያልተመዘገበ ውል መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ስለመሆኑ ከዚህ በላይ ተመልክቷል፡፡ በተጠሪ እና በአቶ አሊዩ ኡሱ መካከል በቀን 22/11/2011 ዓ/ም ተደርጓል የተባለው ውል በሚመለከተው ተቋም ቀርቦ ባልተመዘገበበት ወይም ንብረቱ በተጠሪ ስም ከዚህ በላይ ከተመለከቱት ፍ/ሕ/ቁጥር 1723፣1727፣2877 እና 2888 ድንጋጌዎች አንጻር ባልተመዘገበበት እና የማነቀሳቀስ የቤቱ ባለሀብትነቱ ባለተረጋገጠበት ሁኔታ አመልካች ተገቢውን ጥንቃቄ ሳያደርጉ ግዥ ፈጽመዋል ተብሎ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2882 እስከ 2884 እና ከፍ/ሕ/ቁጥር 997 ድንጋጌዎች አንጻር ከቅን ልቦና ውጭ ግዥ ፈጽመዋል ተብሎ የቀረበውን ክርክር የሥር ፍርድ ቤቶች ተቀብለው አመልካች ቤቱንና ይዞታውን እንዲትለቅ መወሰናቸው ሕጉን መሠረት ያደረገ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በስለሆነም አመልካች ቤቱን የገዛችው መብት ከለሌው ሰው ከቅን ልቦና ውጭ ነው በማለት እንዲትለቅ የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ከላይ የተመለከቱ የሕግ ድንጋጌዎችን ታሳቢ ያላደረገ በመሆኑ ከፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ለ እና ሸ) እና አንቀጽ10 (1/ሐ እና መ) አንጻር መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ውሳኔ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

1. የሻሸመኔ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 14689፣የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 45377፣የኦሮምያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 407521 የሰጡትን ውሳኔ በማጽናት የኦሮምያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 421547 በቀን 24/08/2015 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፌደረል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመርያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1/ለ) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች አከራካሪ የሆነውን 360 ካ.ሜ ይዞታ እና ቤት ለተጠሪ ሊትለቅ አይገባም ተብሏል፡፡
3. ተጠሪ መብቱን ሥር 1ኛ ተከሳሽ ከነበረው ጀማል ከድር ከመጠየቅ ይህ ውሳኔ አይከለክለውም፡፡
4. የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤት ይላክ፡፡
5. የዚህ ችሎት ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡
6. መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

**ማስታወሻ፡** - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መ/ቁ 251831

ታህሳስ 24 ቀን 2017 ዓ/ም

ዳኞች - ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

ብርቅነሽ እሱባለዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች ፡- ሚስተር ዋንግ ኩንግሆንግ (WANG QINGHONG)

ተጠሪ ፡- ሁአኖ ማኑፋክተሪንግ ሃ/የተ/የግ/ማ (HUANO MANUFACTURING PLC)

መዝገቡ ተመርምሮ ተከለታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለሰበር አቤቱታው ምክንያት የሆነው ክርክር የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው አመልካች ባቀረቡት ክስ ከተጠሪ ጋር ለረዥም ግዜ የቆየ የንግድ ግንኙነት የነበረን በመሆኑ በዚህ ግንኙነት ዉስጥ ተጠሪ በብድር ከወሰደዉ ገንዘብ ላይ 1,360,000.00 (አንድ ሚሊዮን ሶስት መቶ ስልሳ ሺ) የቻይና ገንዘብ (RMB) እንደሚከፈል በመግለፅ በቀን 08-04-2016 እ.ኤ.አ (24-11-2008 ዓ/ም) ማረጋገጫ በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክፍለ ከተማ በሚገኘዉ የራሱ ዋና ማስርያ

ቤት ማህተም በማድረግ በስራ አስኪያጁ አማካኝነት ማረጋገጫ ሰጥቷል፡፡ ነገር ግን ገንዘቡን ሊከፈል ስላልቻለ ተጠሪ 1,360,000.00 (አንድ ሚሊዮን ሶስት መቶ ስልሳ ሺ) የቻይና ገንዘብ (RMB) ክፍያዉ በሚፈፀምበት ወቅት በሚኖረዉ የዉጭ ምንዛሬ ታስቦ በኢትኢዮጵያ ብር ከህጋዊ ወለድ እና ወጭና ኪሳራ ጋር እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ በሰጠው መልስ አመልካች ለክሱ መሰረት ያደረገዉ የክፍያ ሰነድ ላይ ክፍያዉ ይፈፀም የሚለዉ ለአመልካች ሳይሆን ለየዋንግ ኩንግሆንግ ዩ ዞንግ ኒያኦ (ፋጂኦን) አዉትዶር ፕሮዳክሽን ኩባንያ ስለመሆኑ ሰነዱ የሚያስረዳ በመሆኑ አመልካች ክሱን ለማቅረብ የሚያስችል መብት ወይም ጥቅም የላቸዉም የሚል መጀመርያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡

የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያው ላይ ግራቀኝን አከራክሮ ባሳለፈው ብይን ለክሱ ምክንያት የሆነዉ ክፍያ የተጠየቀበት ሰነድ ላይ ተጠሪ ክፍያ ይክፈል የሚለዉ ለየዋንግ ኩንግሆንግ ዩ ዞንግ ኒያኦ (ፋጂኦን) አዉትዶር ፕሮዳክሽን ኩባንያ እንጂ ለአመልካች አይደለም፤ አመልካች ድርጅቱ የንግድ ኩባንያ አይደለም ቻይና ዉስጥ የሚገኝ የአመልካች የንግድ ድርጅት ነዉ በማለት ይከራከሩ እንጂ አመልካች ከዚህ ድርጅት ጋር ያላቸዉን ግንኙነት ወይም ድርጅቱ የራሳቸው የአመልካች ስለመሆኑ የሚያስረዳ ማስረጃ ያላቀረቡ በመሆኑ አመልካች ለክሱ መነሻ የሆነዉን ሰነድ መሰረት በማድረግ ክፍያ ለመጠየቅ የሚያስችል መብት ወይም ጥቅም የላቸዉም በማለት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 33(2) እና 244 መሰረት ብይን ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ብይን ቅር ተሰኝተዉ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱ የቀረበዉን ይግባኝ አቤቱታ መርምሮ የስር ፍርድ ቤት ያሳለፈው ብይን ጉድለት የለበትም በማለት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 337 መሰረት ይግባኙን ሰርዟል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው፡፡ አመልካች ባቀረቡት የሰበር ማመልከቻ በስር ፍርድ ቤት ከሰነድ ማስረጃ በተጨማሪ ዉሉን ለማብራራት ምስክሮችን ዘርዝረን አቅርበን እያለ ምስክሮች ሳይሰሙ አመልካች መብትና ጥቅም የላቸዉም ተብሎ የተሰጠዉ ብይን መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነዉ፡፡ የዉጭ አገር ድርጅት አገር ዉስጥ ሳይመዘገብ በሌላ ሰዉ ላይ ክስ ሊያቀርብ እንደማይችል እና ህጋዊ ሰዉነት ሊኖረዉ እንደማይቸል ጠቅሰን (YU ZHONG NIAO (FUJIAN) OUTDOOR PRODUCTS CO., LTD በስሙ ክስ ሊቀርብ ስለማይችል ክሱ የቀረበዉ በአመልካች ስም ነዉ በማለት ከንግድ ህጉ አንቀፅ 555 እስከ 560 ያሉ ድንጋጌዎችን መሰረት በማድረግ ያቀረብነዉ ክርክር ታልፎ ክስ ለማቅረብ መብት ወይም ጥቅም የላችሁም መባሉም መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ያሳለፉት ብይን ተሽሮ በፍሬ ጉዳይ ላይ አከራክሮ እንዲወሰን መዝገቡ ወደ ስር ፍርድ ቤት ይመለስልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

ቅሬታው ተመርምሮ አመልካች ዩ ዞንግ ኒያኦ (ፋጂኦን) አዉትዶር ማኑፋክቸሪንግ ኮ ሊሚትድ ከተጠሪ እና ሌላ አካል እ.ኤ.አ በ08-04-2016 በአዲስ አበባ ቦሌ ክፍለ ከተማ ባደረጉት ስምምንት መሰረት ባለመከፈሉ ተጠሪ የቻይና ገንዘብ (RMB) 1,360,000 እንዲከፈላቸዉ ያቀረቡት ክስ ፍርድ ቤቱ ክፍያ ለመጠየቅ የሚያስችል መብት ወይም ጥቅም እንዳላቸዉ አላስረዱም በማለት ዉድቅ በማድረግ የደረሰበትን ድምዳሜ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች አንጻር ለመመርምር ሲባል ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ ታዟል፡፡ ነገር ግን ተጠሪ መጥርያ የደረሰው ስለመሆኑ የቃለ መሃላ ማረጋገጫ ቀርቦ መልስ ያላቀረበ በመሆኑ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡ መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረው በዚህ ሁኔታ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን በበኩላችን የአመልካች ክስ መብት ወይም ጥቅም የላቸውም ተብሎ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ የተሰጠው ብይን ከአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ይዘትና ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ካላቸው የህጉ ድንጋጌዎች አንፃር ተገቢ መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደሚታወቀው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ በዋናው ህግ የተቀመጡትን መብትና ግዴታዎች ወደ ተግባር ለመለወጥ እንዲያስችል ታስቦ የተዘረጋ ስርዓት ነው፡፡ ከሳሽ የሆነው ወገንም በከሳሽነት ተሰይሞ ክርክሩ እንዲቀጥል ለማድረግ አንደ ክርክሩ በማስረጃ አስደግፎ ቢያስረዳ ከህግ ወይም ከውል የመነጨ መብትና ግደታ ያለ መሆኑን ለማመልከት በሚያስችል ደረጃ ክሱ ተዘጋጅቶ መቅረብ እንዳለበት ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33/2/ እና 33/3/ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች ክስ ያቀረቡት ተጠሪ በቀን 08-04-2016 እ.ኤ.አ (24-11-2008 ዓ/ም) ስለዕዳው የፅሁፍ ማረጋገጫ በራሱ ዋና ማስርያ ቤት ማህተም በማድረግ በስራ አስኪያጁ አማካኝነት ሰጥቶ ነገር ግን ገንዘቡን ያልከፈለ በመሆኑ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡ ከአቤቱታቸው ጋር ተጠሪ እንዲሁም ሌላ አካል ጋር እ.ኤ.አ በ08-04-2016 ያደረጉት ስምምንት እና ሌሎች ማስረጃዎች ተዘርዝረው ቀርበዋል፡፡ ይህ የአመልካች አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 33/2/ እና 33/3/ እንደተደነገገው ከስምምነቱ የመነጨ መብትና ግዴታ ያለ መሆኑን ለማመልከት የሚያበቃ ክርክር እንዳቀረቡ አስረጂ ሲሆን ተጠሪ ዳኝነት የተጠየቀበትን ገንዘብ ለአመልካች የመክፈል ኃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም የሚለው ጭብጥ ውሳኔ የሚያገኘው የግራቀኙ ዝርዝር ክርክር እና ማስረጃ ታይቶ ሊሆን ይገባል፡፡

እንደሚታወቀው ኃላፊነትን የተመለከተ ውሳኔ ሊሰጥ የሚገባው የፍሬ ነገር ክርክርና ማስረጃ ታይቶ ነው፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አወሳሰንን በተመለከተ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 244 እንዲሁም 245(1) እና (2) እንደተደነገገው ተከሳሽ ለክሱ መቃወሚያ ባቀረበ ጊዜ ፍርድ ቤቱ መቃወሚያውን ተቀብሎ ሌላው ተከራካሪ ወገን በጉዳዩ ላይ የሚያቀርበውን ክርክር ከሰማ በኋላ ውሳኔ ለመስጠት ተገቢ መስሎ የሚገምተውን ማስረጃ በመመርምር የቀረበው መቃወሚያ በተገቢና በቂ በሆነ ማስረጃ የተደገፈ መሆን አለመሆኑን በማረጋገጥ ህጉን መሰረት በማድረግ ይወስናል፡፡ ይህ ማለት ግን ክሳሽ ወገን በፍሬ ነገር ደረጃ

ማሳሰቢያ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

የሚያቀርበው ክርክር እና ማስረጃ እንኳ ሳይታይ ተከሳሽ ለክሱ የሚኖርበትን ኃላፊነት በተመለከተ ያቀረበው የፍሬ ነገር ይዘት ያለው ክርክር ታይቶ ክሱ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ ይደረጋል ማለት አይደለም፡፡ በዚህ መልኩ ክሱን በመቃወሚያ መወሰን ስለ ክርክሩ አመራር የተዘረጋውን ስርዓት የተከተለ ካለመሆኑም በላይ የከሳሹን መብት የሚያጣብብ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፡፡

በአጠቃላይ አመልካች ያቀረቡት ክስ ሙሉ ይዘቱ ሲታይ ተጠሪ በቀን 08-04-2016 እ.ኤ.አ (24-11-2008 ዓ/ም) ስለዕዳው የፅሁፍ ማረጋገጫ ሰጥቶ ገንዘቡን ያልከፈለ በመሆኑ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት የቀረበ በመሆኑና ክሱን ለማስረዳት አመልካች ከተጠሪ እንዲሁም ሌላ አካል ጋር ያደረጉት ስምምንት እና ሌሎች ማስረጃዎች የተመለከቱ በመሆኑ አመልካች ክሱን ለማቅረብ መብትና ጥቅም የላቸውም የሚባልበት የህግ ምክንያት የለም፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ አድርጌያለሁ በማለት የተሰጠው ብይን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 33/2/፣33/3/፣ 231/1/ሀ/፣ 244 እና 245 ድንጋጌዎችን ይዘትና ትክክለኛ አፈፃፀም የተከተለ ባለመሆኑ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎትም ይህን ሳያርም ማለፉ የሚነቀፍ ነው፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 242685 ጥር 06 ቀን 2014 ዓ/ም የሰጠዉ ብይን፤ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 219842 ሐምሌ 07 ቀን 2015 ዓ/ም ያሳለፈው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሰረት ተሸሯል፡፡
2. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ የግራቀኙን የፍሬ ነገር ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ተገቢውን እንዲወስን ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ስ/ህ/ቁ 341(1) መሰረት መልሰናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
4. ውሳኔው ጥር 9/2017 ዓ.ም በችሎት ተነቧል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 253101

ታህሳስ 25 ቀን 2017ዓ/ም

ዳኞች :- ገበየሁ ፈለቀ

ደረጀ አያና

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

ብርሃኑ መንግሥቱ

አመልካቾች፡- የአቶ ከበደ ተክለማርያም ወራሾች፡-

1 አቶ ደረጀ ከበደ
2 አቶ ገዛኸኝ ከበደ
3 አቶ ግርማ ከበደ
4 አቶ ሰለሞን ከበደ

ተወካይ ደረጀ ከበደ ቀረቡ

ተጠሪዎች :- 1 አቶ ደረጀ ተስፋዬ
2. ወ/ሮ ቤተልሂም ተስፋዬ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ማጣራትን ተከትሎ የቀረበ የሚስት የንብረት ድርሻን የሚመለከት ነው፡፡ክርክሩ የተጀመረው በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን የአመልካቾች አዉራሽ ሟች አቶ ከበደ

ተክለማሪያም አመልካች፣የአሁኑ ተጠሪዎች በሌላ በኩል ተጠሪዎች በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአመልካቾች አውራሽ በስር ፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያቀረቡት አቤቱታ ይዘት በአጭሩ ልጃቸው ሟች ወ/ሮ ጥሩዓለም ከበደ ልጅ ሳይወልዱ በመሞታቸው ከባለቤታቸው አስር አለቃ ተስፋዬ ደስታ ጋር ያፈሩት በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 12 የቤት ቁጥር 682 የሆነው ንብረት እና ከቤቱ የተሰበሰበው የኪራይ ሀብት በውርስ አጣሪ ተጣርቶ የድርሻዬ እንዲለይ በሚል ያቀረቡ ሲሆን የሟቿ አባት የሆኑት አቶ ከበደ ተክለማሪያም በመሞታቸው አመልካቾች በተተኪ ወራሽነት ወደ ክርክሩ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ተጠሪዎችም በቀረበው አቤቱታ ላይ መልስ በመስጠት የአቤቱታው መነሻ የሆነው የውርስ ሀብቱም ተጣርቶ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡በውርስ አጣሪው ተጣርቶ የቀረበው ርፖርት ይዘትም የአስር አለቃ ተስፋዬ ደስታ በመ/ቁ 158482 ህዳር 03 ቀን 2013 ዓ.ም የውርስ ሀብት ተጣርቶ በጸደቀው የውርስ ሀብት ሪፖርት አስር አለቃ ተስፋዬ ደስታ ሰኔ 09 ቀን 1995 ዓ.ም ባደረጉት ኑዛዜ መሰረት የክርክር መነሻ በሆነው ቤት እና ይዞታ ላይ የሟች ወ/ሮ ጥሩዓለም ከበደ ድርሻ 1/4ኛ ነው የሚል ውሳኔ የተሰጠ በመሆኑ አመልካቾች የሟቿን ድርሻ የቤቱን እንደዚሁም ከኪራይ የሚገኘውን ገቢ 1/4ኛ ድርሻ እንዲካፈሉ የሚል ነው፡፡ግራ ቀኙም በቀረበው የውርስ አጣሪ ሪፖርት ላይ ያላቸውን አስተያየት የሰጡ ሲሆን ፍ/ቤቱም የሟች አስር አለቃ ተስፋዬ ደስታ የውርስ ሀብት በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 158482 ላይ ተጣርቶ የፀደቀ ሲሆን በዚህ የጸደቀው የውርስ አጣሪ ሪፖርት ላይ የውርስ ሀብት የሆነውን ቤት ሟች አስር አለቃ ተስፋዬ ደስታ በሰኔ 09 ቀን 1995 ዓ.ም ባደረጉት ኑዛዜ በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 12 የቤት ቁጥር 682 ከሆነው ቤት እና ይዞታ ላይ የሟች ወ/ሮ ጥሩዓለም ከበደ ድርሻ 1/4ኛ መሆኑን ፍ/ቤቱ የቀረበው በውርስ አጣሪ ሪፖርት ተረጋግጧል፣አመልካቾችም ይህን ውሳኔ አላሻሩም፣ከቤት ቁጥር 682 ላይ የሟች ወ/ሮ ጥሩዓለም ከበደ የሚስትነት ድርሻ ግማሽ ድርሻ እንደሆነ የሚገልጽ ውሳኔ አላቀረቡም፣አመልካቾች ይህ ውሳኔ ስለመሻሩም ያቀረቡት ማስረጃ የለም፣ ወ/ሮ ጥሩዓለም ከበደ የሟች አስር አለቃ ተስፋዬ ደስታ ሚስት ስለመሆኗ እና ቤት እና ይዞታውን በጋራ አፍርተዋል በሚል የተሰጠ ውሳኔ አልቀረበም፣ ሟች ወ/ሮ ጥሩዓለም ከበደ ከሟች አስር አለቃ ተስፋዬ ደስታ ጋር በመሆን ያፈሩ በመሆኑ ግማሹ የሟች ወ/ሮ ጥሩዓለም ከበደ የሚስትነት ድርሻ ሊሆን ይገባል የሚል ክርክር ሊቀርብ የሚገባው በቤተሰብ ችሎት እንጂ በዚህ በተያዘው ችሎት ባለመሆኑ የሟች ወ/ሮ ጥሩዓለም ከበደ ድርሻ ከሆነው 1/4ኛ ድርሻ ላይ አመልካቾች እያንዳንዳቸው 1/4ኛ ድርሻ አላቸው።የቤት ኪራይን ገቢን በተመለከተ የተሰበሰበው ገቢ በአጠቃላይ ብር 444,400 ስለሆነ ከዚህ ገንዘብ ላይ ሟች ወ/ሮ ጥሩዓለም ከበደ ድርሻ ብር 111,100 በመሆኑ ሟች ወ/ሮ ጥሩዓለም ከበደ ድርሻ ላይ አመልካቾች እያንዳንዳቸው 1/4ኛ ማለትም ብር 27,775 ብር የሚደርሳቸው ሆኖ ለተለያዩ ጉዳዮች የወጣው ወጪ ብር 108,259.11 በመሆኑ የሟች ወ/ሮ ጥሩዓለም ከበደ ድርሻ ብር 27,064.78 ስለሆነ ከዚህ ላይ አመልካቾች

እያንዳንዳቸው ብር 6943.75 የሚለከፍሉት ውርስ ሃብት ዕዳ ይሆናል በማለት በውርስ አጣሪ የቀረበውን ሪፖርት አጽድቆታል፡፡

አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታቸውን ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም በመ/ቁ 36691 ሰኔ 05 ቀን 2015 ዓ.ም በሰጠው ብይን ባላሻሩበት በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ ስህተት የለበትም በማለት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

አመልካቾችም የተሰጠው ውሳኔ ላይ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን የቀረበው አቤቱታ ይዘትም በአጭሩ ወ/ሮ ጥሩዓለም ከበደ የሟች አስር አለቃ ተስፋዬ ደስታ ሚስት ስለመሆናቸው ሐምሌ 13 ቀን 1996 ዓ.ም የተሰጠው የሚስትነት ማስረጃ ለውርስ አጣሪ እንዲሁም ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረብን ከመሆኑም በላይ ተጠሪዎች በስር ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር የካዱት ነገር የለም፡፡ይህ ከሆነ ሟች ወ/ሮ ጥሩዓለም ከበደ በሚስትነታቸው በተሻሻለው ቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 63(1) መሠረት ከባለቤታቸው ጋር በትዳር ወቅት ያፈሩት የውርስ ሀብት ላይ ያላቸው ድርሻ 1/2ኛ እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡ይህ በሆነበት የሥር ፍርድ ቤቶች ወ/ሮ ጥሩአለም ከበደ ሚስት ስለመሆናቸው ክርክር ባልተነሳበት እና ችሎቱ ራሱ ከሕጉ ጋር አገናዝቦ የሚስትነት ድርሻ ምን ያህል እንደሆነ በህጉ መሠረት መወሰን ሲገባው የሕግ ግምት የሚስትነት ድርሻ በቤተሰብ ችሎት እንጂ በዚህ ችሎት አይታይም በሚል የደረሰበት መደምደሚያ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 35(1) ላይ የተደነገገውን የሴቶችን መብት እንደዚሁም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 45905፣79871 እና በሌሎች በርካታ መዝገቦች የሰጣቸውን አስገዳጅ ውሳኔዎችን የሚቃረን በመሆኑ ሊታረም ይገባል፡፡በስር ፍርድ ቤቶች የተጠቀሰውና በመ/ቁ 154882 የነበረው ክርክር ላይ ተሳታፊ ያልነበርን ሲሆን መዝገቡም የወራሽነት ድርሻ ማረጋገጫ ብቻ በመሆኑ በዚህ መልኩ የወራሽነት ድርሻ ላይ የተሰጠን ውሳኔ በሌላ ክርክር ተቃውሞ አቅርቦ መከራከር ከሚቻል በስተቀር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ ቁ 358 መሠረት መቃወም አመልካች ሆነን ልንገባ እንደማንችል ከላይ የተጠቀሱት የሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች የሰጠበት ጉዳይ ነው፡፡ይህ የሰበር አቤቱታ ቅሬታ የቀረበበት የመዝገብ ቁጥር 117089፣የመዝገብ ቁጥር 154882 ከመከፈቱ አስቀድሞ የተጀመረ መዝገብ ሆኖ እያለ አመልካቾች በቀረበው የውርስ አጣሪ ሪፖርት ላይ ያቀረብነው አስተያየት ሳይመለከትልን የውርስ አጣሪ ከስልጣናቸው በላይ የደረሱበትን መደምደሚያ በመቀበል የውርስ አጣሪ ሪፖርቱን ማፅደቁ አላግባብ ነው፡፡የቤት ኪራዩን በተመለከተም ተጠሪዎች የክርክር መነሻ የሆነው ቤት በማከራየት የሚጠቀሙበት የገንዘብ መጠን በባለሙያ የተጣራ ሪፖርት እያለ የውርስ አጣሪዋ አመልካቾች ባላውቀነው እና አስተያየት ባልሰጠንበት ሌላ ሪፖርት በማዘጋጀት ታህሳስ 10 ቀን 2015 ዓ.ም አዘጋጅተው ባቀረቡት ሪፖርት ደግሞ የሚከራዩት ቤቶች ሁለት ክፍል ቤቶች ብቻ እንደሆነ ጠቅሰው ያቀረቡት የኪራይ መጠን በተመለከተ አመልካቾች ለሥር ፍርድ ቤቱ

ቅሬታችንን አቅርበን እያለ ያቀረብነውን ቅሬታ በአግባቡ ሳይሰማን ሪፖርቱን ማፅደቁ ጭምር የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲታረምልን የሚል ነው፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም አመልካቾች ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ መነሻ በማድረግ አመልካቾች የሟች ወ/ሮ ጥሩዓለም ከበደ ተተኪ ወራሾች ሲሆኑ ወ/ሮ ጥሩዓለም ከበደ ከሟች አስር አለቃ ተስፋዬ ደስታ ጋር በትዳር የቆዩ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤት መመልከቱ ሲታይ ንብረቱ የጋራ የባልና ሚስት ንብረት ስለመሆኑ የሕግ ግምት የሚወሰድብት ነው ወይስ አይደለም፤ተጠሪዎች የሕግ ግምቱን ማስረጃ በማቅረብ በማስተባበል የባል የግል ንብረት ስለመሆኑ ማስረዳት አለማስረዳታቸው፤የአስር አለቃ ተስፋዬ ደስታ የውርስ ሀብት ሪፖርት የሕግ ግምቱን ለማስተባበል የሚችል መሆን አለመሆኑ፤ አመልካቾች በሟች አስር አለቃ ተስፋዬ ደስታ የውርስ ሀብት ማጣራት ያልተሳተፉ ከመሆኑ አንጻር የውርስ ሪፖርቱ እንደጸና ፍርድ ተቆጥሮ አመልካቾችን ያስገድዳል መባሉ ሕጋዊ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ተጠሪዎች የሰበር አቤቱታው ከዚህ ትዕዛዝ ጋር ደርሷቸው መልስ በጽሁፍ እንዲያቀርቡ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡

1ኛ ተጠሪም ነሀሴ 14 ቀን 2016 ዓ.ም በሰጡት መልስ በመዝገብ ቁጥር 117089 በነበረው ክርክር ሟች አሥር አለቃ ተስፋዬ ደስታ ባደረጉት ኑዛዜ ላይ የአመልካቾችን አውራሽ በኑዛዜ ተካፋይነት ድርሻ ያላቸው መሆኑን በግልጽ አስቀምጧል፡፡በኑዛዜ ማስረጃው መሰረት ሟች ወ/ሮ ጥሩዓለም ከበደ የኑዛዜ ወራሽ ናቸዉ፣በሥር ፍ/ቤት ሚስት ናቸው የሚል ቢኖርም ሚስትነት ብቻውን የንብረት ተካፋይ አያደርግም፣ሟች ወ/ሮ ጥሩዓለም ከበደ በሚስትነታቸው ለንብረቱ መፈራት ያደረጉት አስተዋጽኦ በግልጽ ያልተቀመጠ በመሆኑ ሚስት በመሆን ብቻ የንብረት ተካፋይ ለመሆን የሚቻል አይደለም፣ሟች ወ/ሮ ጥሩዓለም ከበደ የሟች አስር አለቃ ተስፋዬ ደስታ ሚስት መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የሚስትነት ውሳኔም ሆነ ሌላ የሰነድ ማስረጃ አልቀረበም፣ሟች ወ/ሮ ጥሩዓለም ከበደ ሚስት ስለመሆናቸው ተጨባጭ ማስረጃ ባልቀረበበት ንብረቱ የጋራ የባል ሚስት ንብረት ይሆናል በሚል የህግ ግምት ሊወሰድ አይገባም፣ተጠሪዎች ንብረቱ የባል የግል ንብረት ስለመሆኑ ማስረዳት አይጠበቅብንም፣ንብረቱ የባልና ሚስት በጋራ የተፈራ ነው የሚለውን የማስረዳት ግዴታ እና ሸክም ያለባቸው አመልካቾች ሲሆኑ አውራሻቸው ሟች ወ/ሮ ጥሩዓለም ከበደ ክርክር የተነሳበትን ንብረት በሚስትነት ስለማፍራቷ በሌላ ችሎት አረጋግጠውና አስወስነው የማቅረብና የማስረዳት ኃላፊነት ያለባቸው አመልካቾች እንጂ ተጠሪዎች አይደለንም፣አመልካቾች የውርስ ሀብት ሪፖርቱን ሊያስተባብል የሚችል አንዳችም ማስረጃ አላቀረቡም፣የውርስ ሀብት ሪፖርቱ ያልተስተባበለ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም፣በፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 83007 በተሰጠ ውሳኔ በህግ አግባብ እስካልተሻረ ድረስ የውሳኔው አስገዳጅነትና ተፈጻሚነት በባለጉዳዮች ላይ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን በማናቸውም አስፈጻሚ አካላትና በማናቸውም ፍ/ቤት ላይ ጭምር አስገዳጅ ነው

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

በሚል በተሰጠው ውሳኔ መሰረት በመዝገብ ቁጥር 158482 የተሰጠው ውሳኔ እንደጸና ፍርድ የሚቆጠር ነው፡፡አመልካቾችም ዳኝነት የሚጠይቁበት ንብረት የሟች አሥር አለቃ ተስፋዬ ደስታ በግል የተፈራ ንብረት ላይ በመሆኑ እንዲሁም ኑዛዜውም ያለና የጸና በመሆኑ አመልካቾችን የማስገደድ ህጋዊ መብት አለው፡፡በመዝገብ ቁጥር 158482 ላይ አመልካቾች ተሳትፎ ባይኖራቸው እንኳን ውሳኔውን ሊያስተባብል የሚችል ውሳኔ ወይም ማስረጃ ሊያቀርቡ ይገባል፣አመልካቾች በቀረበው አቤቱታ ላይ የጠቀሷቸው የሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች አሁን ከተያዘው ክርክር ጋር አንዳችም ተመሳሳይነት የላቸውም፣ሊያስገድድም አይችልም፡፡የቤት ኪራይን በተመለከተ አግባብ ካለው የመንግስት ተቋም አጣርቶ ከቀረበ በኃላ ውሳኔ የተሰጠበት በመሆኑ የቀረበው አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚል ነው፡፡

2ኛ ተጠሪ በአመልካቾች በቀረበው የሰበር አቤቱታ ላይ መልስ እንዲሰጡበት አቤቱታው ከመጥሪያ ጋር የደረሳቸው ቢሆንም መልስ ያልሰጡ በመሆኑ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

አመልካቾችም 1ኛ ተጠሪ በሰጡት መልስ ላይ ነሐሴ 23 ቀን 2016 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ በማቅረብ ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታቸውን አጠናክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን ችሎቱም የግራ ቀኙ ክርክር እና በስር በፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎችን መሰረት በማድረግ መዝገቡን መርምሮታል፡፡መዝገቡን እንደ መረመርነው ሟች ወ/ሮ ጥሩዓለም ከበደ የሟች አስር አለቃ ተስፋዬ ደስታ ሚስት ስለመሆናቸው ሐምሌ 13 ቀን 1996 ዓ.ም ከተሰጠው የሚስትነት ውሳኔ መረዳት የሚቻል ሲሆን በስር ፍርድ ቤትም አላከራከረም፡፡በሟቾች መካከል የነበረው ጋብቻ በሞት የፈረሰ ሲሆን የጋብቻው በሞት መፍረስን ተከትሎ የሚቀርበው የንብረት ክርክር አስመልክቶ ንብረቱ የአንደኛው ተጋቢ የግል ሀብቱ መሆኑን ካላስረዳ በስተቀር ማንኛውም ንብረት በአንደኛው ተጋቢ ስም ብቻ የተመዘገበ ቢሆንም እንኳ የጋራ ሀብት ሆኖ የሚቆጠር ስለመሆኑ በተሻሻለው የፌደራል ቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 63(1) ስር ተደንግጎ የሚገኝ ነው፡፡የተጠቀሰውን የህግ ግምት ለማስተባበል ንብረቱ የግሌ ነው የሚል ተጋቢ ንብረቱ የግሌ እንጂ የጋራ አይደለም የሚል የማስረዳት ግዴታ የሚጠበቅበት ስለመሆኑ የሚያሳይ ነው፡፡ተጠሪዎች የክርክር መነሻ የሆነው ንብረት የሟች አስር አለቃ ተስፋዬ ደስታ የግል ሀብት ነው በሚል የሚከራከሩት ሟቹ የክርክር መነሻ ሆነውን ንብረት በሚመለከት ባለቤታቸው ሟች ወ/ሮ ጥሩዓለም ከበደን ጨምሮ ሰኔ 09 ቀን 1995 ዓ.ም ኑዛዜ ያደረጉ በመሆናቸው የንብረት ክፍፍሉ ሊፈጸም የሚገባው ኑዛዘውን መነሻ በማድረግ ተጣርቶ በቀረበው የውርስ ሪፖርት መሠረት የሟች ወ/ሮ ጥሩዓለም ከበደ ድርሻ 1/4ኛ መባሉ በአግባቡ ነው የሚል ሲሆን አመልካቾች በበኩላቸው በሟች አስር አለቃ ተስፋዬ ደስታ የውርስ ሀብት ማጣራት ያልተሳተፉ ከመሆኑ አንጻር የውርስ ሪፖርቱ እንደማስረጃ እንጂ እንደ ፍርድ ተቆጥሮ አመልካቾችን ሊያስገድድ አይችልም በሚል የሚከራከሩ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ናቸው፡፡አመልካቾች የሟች ወ/ሮ ጥሩ ዓለም ከበደን በመወከል ተሳታፊ ባልሆኑበት ተጠሪዎች የሟች አስር አለቃ ተስፋዬ ደስታ የውርስ ሀብት በመ/ቁ 158482 ህዳር 14 ቀን 2013 ዓ.ም ተጣርቶ ለፍርድ ቤት ቀርቦ እንዲጸድቅ የተደረገ ስለመሆኑ ከስር ፍርድ ቤት ክርክር መረዳት የሚቻል ሲሆን የጸደቀው የውርስ ሀብት እንደ ፍርድ ተቆጥሮ አመልካቾችን የሚያስገድድ ስለመሆን አለመሆኑ መመርመር አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ከውርስ ማጣራት ጋር ተያይዞ በፍርድ ቤት ቀርቦ የጸደቀ የውርስ አጣሪ ሪፖርት በሚመለከት የሟች ወራሾች በተገኙበት የጸደቀ የውርስ ማጣራት ሪፖርት እንደውሳኔ የሚወሰድ ስለመሆኑ በሰበር መ/ቁ 221741 ላይ አስገዳጅ ውሳኔ የተሰጠ ሲሆን በሌላም በኩል የሟች ወራሾች ባልተሳተፉበት ተጣርቶ የሚቀርብ የውርስ ማጣራት ሪፖርት እንደሁኔታው በማስረጃነት የሚያገለግል ሆኖ እንደ ውሳኔ የማይወሰድ ስለመሆኑ በሰበር መ/ቁ 45905 እና ተመሳሳይ ውሳኔዎች አስገዳጅ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የሟች ወ/ሮ ጥሩዓለም ከበደ ተተኪ ወራሽ የሆኑት አመልካቾች የሟች አስር አለቃ ተስፋዬ ደስታ የውርስ ሀብት በመ/ቁ 158482 ህዳር 14 ቀን 2013 ዓ.ም የወ/ሮ ጥሩ ዓለም ከበደን ድርሻ ጨምሮ ሲጣራ ተሳታፊ ያልነበሩ ስለመሆናቸው የተረጋገጠ ሲሆን በዚህ መሠረት የፀደቀ የውርስ አጣሪ ሪፖርት እንደ ውሳኔ የሚወሰድ ሳይሆን በማስረጃነት የሚያገለግል በመሆኑ በውርስ አጣሪው ቀርቦ የጸደቀው ሪፖርት እንደጸና ፍርድ ተቆጥሮ ብቻውን አመልካቾችን ሊያስገድድ የሚችል ሆኖ አልተገኘም፡፡ስለሆነም የቀረበው የውርስ አጣሪ ሪፖርት እንደ አንድ ማስረጃ የሚወሰድ ሆኖ ባለበት በመ/ቁ 117089 ላይ የሟች ወ/ሮ ጥሩ ዓለም ከበደ የውርስ ሀብት እንዲጣራ ሲቀርብ የክርክር መነሻ ሆነው ቤት እና ከቤቱ የሚገኝ የኪራይ ገቢ በሚመለከት የተጋቢ ሟቾች የጋራ ሀብት ስለመሆን አለመሆኑና የሟቿ ወራሾች የክርክር መነሻ ከሆነው ንብረትና ከቤቱ የሚገኘው የቤት ኪራይ ሊያገኙ የሚገባውን የድርሻ መጠን ከሌሎች ማስረጃዎች ጋር ሳይጣራ የሟች ወ/ሮ ጥሩዓለም ከበደ ድርሻ 1/4ኛ ነው በሚል የተወሰነበት በአግባቡ አይደለም ብለናል፡፡

ሲጠቃለል ሟች ወ/ሮ ጥሩዓለም ከበደ ከሟች አስር አለቃ ተስፋዬ ደስታ ጋር በትዳር የቆዩ ስለመሆናቸው በስር ፍርድ ቤት መመልከቱ ሲታይ የክርክር መነሻ የሆነው ቤት እና ከቤቱ የሚገኘው ኪራይ ገቢ የጋራ የባልና ሚስት ንብረት ስለመሆኑ የሕግ ግምት የሚወሰድብት ነው ወይስ አይደለም፤ ተጠሪዎች የሕግ ግምቱን ማስረጃ በማቅረብ በማስተባበል የክርክር መነሻ የሆነው የግል ንብረት ስለመሆኑ ስለማስረዳት አለማስረዳታቸው እንደዚሁም የአስር አለቃ ተስፋዬ ደስታ የውርስ ሀብት ሪፖርት የሕግ ግምቱን ለማስተባበል የሚችል መሆን አለመሆኑ ተጣርቶ ሊወሰን ሲገባ በአግባቡ ሳይጣራ በሟች አስር አለቃ ተስፋዬ ደስታ የተደረገውን ኑዛዜ መነሻ በማድረግ ተጣርቶ በቀረበው የውርስ አጣሪ ሪፖርት መሰረት ሟች ወ/ሮ ጥሩ ዓለም ከበደ ከንብረቱ ያላቸው ድርሻ 1/4ኛ በመሆኑ አመልካቾች ይህንኑ ድርሻ የሚገባቸው ነው በሚል የተወሰነበት አግባብ በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ

ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4)(ሸ) እና 10(1)(ሀ) መሠረት መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 306691 ሰኔ 05 ቀን 2015 ዓ.ም እንደዚሁም በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መ/ቁ 117089 መጋቢት 01 ቀን 2015 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1)(ለ) መሠረት ተሽሯል፡፡

2. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተዘጋውን የመዝገብ ቁጥር 117089 በማንቀሳቀስ የሟች አስር አለቃ ተስፋዬ ደስታ በመ/ቁ 158482 ተጣርቶ የጸደቀውን ሪፖርት እንደ አንድ ማስረጃ በመውሰድ ከላይ በውሳኔው ይዘት ውስጥ በተገለጸው መሠረት የክርክር መነሻ የሆነውንና በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 12 የሚገኘውን የቤት ቁጥር 682 የሆነው ቤት እና ይዞታ እንደዚሁም ከቤቱ የሚገኘው የኪራይ ገቢ በሚመለከት በግራ ቀኙ የቀረቡትን ማስረጃዎች እና አግባብነት ባለው ማስረጃ ጭምር በመመዘን የሟች ወ/ሮ ጥሩዓለም ከበደ ድርሻ 1/2ኛ ነው ወይስ 1/4 ስለመሆኑ በማጣራት ሕግን መሰረት ያደረገ ዉሳኔ እንዲሰጥ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2012 አንቀጽ 9/2 መሰረት መልሰንለታል፡፡

3. በዚህ ችሎት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

1. በዉሳኔዉ መሰረት እንዲፈጸም የውሳኔው ግልባጭ ለፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡

2. የመ/ቁጥር 158482 ወደ ፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይመለስ፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፣ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት


የሰበር መዝገብ ቁጥር - 253253

ቀን - 28/04/2017 ዓ.ም

ዳኞች - ሽመክት አሰፋ

እንዳሻው አዳነ

ዓለማየሁ ሹናራ

ዋዚሞ ዋሲራ

ዘውዲቱ ታደሰ

አመልካች - ሶራ ሴኪዩሪቲ ኃ/የተ/የግ/ማ

ተጠሪ - ታቦር ሴራሚክስ ውጤቶች አ/ማህበር

መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው ለምርመራ ስለሆነ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የተጀመረው በሲዳማ ብሄራዊ ክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች ተከሳሽ ተጠሪ ከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የስር ከሳሽ በተከሳሽ ላይ ያቀረበው ክስ ይዘቱ በአጭሩ የፋብሪካውን ደህንነት ለማስጠበቅ የጥበቃ ውል ከተከሳሽ ጋር በ02/05/2014 ዓ.ም መፈፀሙን ተከሳሽ ግዴታውን ባለመወጣት በተለያዩ ጊዜ የከሳሽ ንብረት የተሰረቀ በመሆኑ የንብረቱ ግምት ብር 4,825,295.00 (አራት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሃያ አምስት ሺህ ሁለት መቶ ዘጠና አምስት ብር) ጉዳት ያደረሰ በመሆኑ በፍ/ብ/ህ አንቀፅ 2028 መሰረት እንዲከፍል የሚል ነው፡፡ ከተከሳሽ በኩል ለክሱ የተሰጠው መልስ ይዘቱ በአጭሩ ከሳሽ ተሰረቀብኝ ብሎ ያቀረበው 38 ዕቃ በውላችን መሰረት

ተቆጥሮ ያልተሰጠ ንብረት በመሆኑ በተከሳሽ ጥፋት ጉዳት አልደረሰበትም፡፡ ጠፉ ከተባሉት ንብረቶች ውስጥ በውላችን አንቀፅ 4.2 መሰረት ያልተረከብኩትና የማላውቀው ነው፡፡ ተሰረቀ ከማለት ውጪ ከየትኛው መጋዘን እንደተሰረቀ እና የትኛው እቃ እንደተሰረቀ በስማቸው ዘርዝሮ አለማቅረቡ እቃዎቹ አለመሰረቃቸውን የሚያሳይ ከመሆኑ በተጨማሪ በተለያዩ ቦታ ላይ እርስ በርስ የሚጋጭ የዋጋ ዝርዝር አቅርቧል፡፡ የጠቀሳቸው እቃዎች ለመያዝ ፍቃድ የለውም፡፡ በስርቆት ጥርጣሬ በተደረገ ቆጠራ የከሳሽ ሰራተኞች በኦዲት ይጠየቃሉ እንጂ ከውጪ እየጠበቁ ያሉ ጥበቃዎች ተጠያቂ ሊሆኑ የሚችሉበት አግባብ ስለሌለ ተከሳሽ ለከሳሽ የሚከፍለው ገንዘብ የለም ተብሎ እንዲወሰን የሚል መልስ ከሰጡ በኃላ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አቅርቧል፡፡ ዝርዝሩ በአጭር ከሳሽ ጠፍቶብኛል በሚል ምክንያት በመካከላችን ያለውን ውል በ28/01/2014 ዓ.ም አቋርጦ ያለበትን ውዝፍ ደመወዝ የ 10 ወር 834,652.21 (ስምንት መቶ ሰላሳ አራት ሺህ ስድስት መቶ ሃምሳ ሁለት ብር ከሃያ አንድ ሳንቲም) በተጨማሪ ለተመደቡ ለአራት ጥበቃዎች የ 6 ወር ብር 55,643.47 (ሃምሳ አምስት ሺህ ስድስት መቶ አርባ ሶስት ብር ከአርባ ሰባት ሳንቲም) በውላችን መሰረት ያለማስጠንቀቂያ ውሉን በማቋረጡ ብር 92,739.12 ውል ለማፍረሱ ቅጣት 5,000.00 ብር በአጠቃላይ ብር 990,816.23 (ዘጠኝ መቶ ዘጠና ሺህ ስምንት መቶ አስራ ስድስት ብር ከሃያ ሶስት ሳንቲም) ከሳሽ ለተከሳሽ እንዲከፍል የሚል ነው፡፡

ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን የፅሁፍና የቃል ክርክር ከተጠናቀቀ በኃላ ከሳሽ በውሉ መሰረት የጥበቃ ተጠያቂነትን ወይም ኃላፊነትን ባለመወጣት ጠፍቶብኛል ወይም ተሰርቆብኛል ያለው ዕቃ እንደጠፋ ወይም እንደተሰረቀበት ኃላፊነቱ የተከሳሽ መሆኑ ተረጋግጧል ወይም አልተረጋገጠም? የጠፋው እቃ መጠኑ ምን ያህል ነው? ከሳሽ ለተከሳሽ መክፈል የሚገባው ክፍያ አለ ወይስ የለም? አለ ከተባለ መጠኑ ምን ያህል ነው? ቅጣትና ኪሳራ ተከሳሽ ሊከፍል ይገባል ወይስ አይገባም የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ የከሳሽ የሰውና የሰነድ ምስክሮችን ከመረመረ በኃላ የግራ ቀኙ ውል ፀንቶ ባለበት ተከሳሽ የውል ግዴታውን እንዳልተወጣ ከሳሽ በተሻለ ሁኔታ ያስረዳ መሆኑን ከሳሽና ተከሳሽ ውል ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ ውላቸውን ካቆሙበት ለ28/01/2014 ዓ.ም ድረስ በተለያየ ጊዜ የጥበቃዎች ጥንቃቄ ማነስ የተሰረቀ እቃዎችና በዝርዝር የተገለፁት ንብረቶች ለመሰረቃቸው የውላቸው አንቀፅ 3.2 መሰረት እና በፍ/ብ/ህ አንቀፅ 2028 እና 2029 መሰረት በስራው ላይ በተፈጠረው ጉድለት ተከሳሽ ተጠያቂ ነው፡፡

ከሳሽ ከጠየቀው ዳኝነት ውስጥ በ01/02/2014 ዓ.ም እንደተሰረቀ ገልፆ የቀረበውን ገንዘብ ተቀንሶ የሚቀረው ማለትም ከብር 4,825,290 ውስጥ ብር 161,090 ሲቀነስ ብር 4,664,200 ተከሳሽ ሊከፍል ይገባል፡፡ በመቀጠል 2010 ዓ.ም እና የካቲት 2013 ዓ.ም ጀምሮ ውሉ እስከተቋረጠበት

ቀን 28/01/2014 ዓ.ም ድረስ መከፈል የነበረበት በጠቅላላ የ 8 ወርና በኃላ የተጨመሩ ሰራተኞች የ 9 ቀንና የ 6 ወር ክፍያ በውላቸው መሰረት ከሳሽ ለተከሳሽ ከዚህ በፊት ሲከፍል በቆየው ክፍያ አከፋፈል ስርአት መሰረት ሊከፍል ይገባል፡፡ ቅጣትና ኪሳራ በማስረጃ ያልተረጋገጠ ስለሆነ ተከሳሽ ሊከፍል አይገባም ሲል ወስኗል፡፡

ተከሳሽ በዚህ ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቧል፡፡ ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ በፖሊስ ምርመራ መዝገብ ላይ ከሳሽ በ08/11/2013 ዓ.ም በፃፈው ፅሁፍ የድርጅቱ ንብረት ብር 1,395,520.00 (አንድ ሚሊዮን ሶስት መቶ ዘጠና አምስት ሺህ አምስት መቶ ሃያ ብር) እንዳጠፋ የገለፀ በመሆኑ ከሳሽ ከቅን ልቦና ወጪ በሆነ ሁኔታ የጠፋውን ንብረት መጠን አጋኖ ያቀረበ ስለሆነ የካሳ ክፍያ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል መሆን ስለሚገባው ተከሳሽ የጠፋውን ንብረት ዋጋ ብር 1,590,310.00 (አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ዘጠና ሺህ ሶስት መቶ አስር ብር) እንዲከፍል በማለት አሻሽሎ ወስኗል፡፡

የአሁን ሰበር ቅሬታ የቀረበው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አሻሽሎ በወሰነው ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነው፡፡ የሰበር ቅሬታ ይዘቱ በአጭሩ በግራ ቀኞችን መካከል የነበረው ውል አንቀፅ 3.3 መሰረት በከሳሽ ንብረት ላይ የደረሰውን ጉዳት ለመካስ የምንገደደው በውላችን አንቀፅ 4.2 መሰረት በመጋዘን የተቀመጠ ንብረት ቁልፍ ተሰብሮ የተወሰደ ሲሆን ነው፡፡ ከመጋዘን ውጪ የተቀመጡ ንብረቶችን ከሳሽ በማያሻማ መልኩ ቆጥሮ ካስረከበኝ ንብረቶች ውስጥ ጠፍቶ ሲገኝ ብቻ ነው፡፡

ተጠሪ የማስረዳት ግዴታውን ባልተወጣበትና ንብረቶች ባልጠፉበት ሁኔታ በአመልካችና ተጠሪ መካከል ከነበረው ውል ድንጋጌዎች ውስጥ ተጠሪን የሚጠቅሙ ድንጋጌዎች ብቻ በመውሰድ የተጠሪን ተነፃፃሪ የውል ግዴታ ከግምት ውስጥ ሳያስገባ የወሰነበት ውሳኔ በሰበር ቅፅ 19 በመዝገብ ቁጥር 103910 እና ቅፅ 13 በመዝገብ ቁጥር 13 በመዝገብ ቁጥር 69915 የሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሚጣረስ ስለሆነ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፡፡

አመልካች ካሳ እንዲከፍል የተጠየቀ ንብረቶች ያልጠፉ ስለመሆናቸው በአመልካች መከላከያ ማስረጃና የስር ጠቅላይ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ ባስመጣው በፖሊስ ምርመራ መዝገብ ተረጋግጦ እያለ ላልጠፋ ንብረት ትክክለኛ ዋጋቸው ሳይታወቅ አመልካች ካሳ እንዲከፍል የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ በቅፅ 15 በመዝገብ ቁጥር 79794 የሰጠውን የህግ ትርጉም የሚጣረስ በመሆኑ ስህተት ነው፡፡ ካሳ እንድከፍል የጠፉ እያንዳንዱ ንብረቶች የጠፉ መሆን አለመሆኑ የጠፉ ናቸው የሚባል ከሆነም የንብረቶች ትክክለኛ ዋጋ ስንት እንደሆነ ከገለልተኛ ወገን መግለጫ ተጠይቆ እንዲወሰን የሚል ነው፡፡

ይህ ችሎት አመልካችና ተጠሪ ካደረጉት የጥበቃ አገልግሎት ውል አንፃር ተጠሪ ጠፍተዋል በማለት የገለፃቸው 38 እቃዎች እና በስር ፍርድ ቤቶች ከተረጋገጠው አንፃር አመልካች ሁሉንም ንብረት የመጠበቅ ኃላፊነት አለበት ሲል የተሰጠውንና መጠኑን በተመለከተ የተወሰነበት አግባብነት በግራ ቀኙ መካከል ከተደረገው የውል ስምምነት አንፃር ለመመርመር ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ በ 2/12/2016 ዓ.ም በ 04 ገፅ አቅርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

ይዘቱ በአጭሩ የተጠሪ ንብረት መጥፋቱ በስር ፍርድ ቤት በማስረጃ ተረጋግጦ አመልካች ይህን ባለማስተባበሉ የተወሰነ ውሳኔ ስለሆነ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት አልተገኘም፡፡

አመልካች በውላችን መሰረት የተጠሪ ሙሉ ግቢን ለመጠበቅ ግዴታ የገባ በመሆኑ ተጠሪ ሊወጣ የሚገባው ተነፃፃሪ ግዴታ ባለመኖሩ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው፡፡ በውላችን መሰረት አመልካች ሊጠብቀው የሚገባ ንብረት በግቢ ውስጥ በመጋዘን ውስጥ እና ከመጋዘን ውጪ ያሉ ንብረቶች በሙሉ በመሆኑ ከዚህ አንፃር በተጠሪ ቅጥር ግቢ ውስጥ ስለጠፉ ንብረቶች አመልካች ኃላፊነት አለበት ተብሎ የተሰረቁ ንብረቶች ግምት እንዲከፍል መወሰኑ በአግባቡ ስለሆነ የአመልካች ቅሬታ ውድቅ እንዲደረግ፤ መጠኑን በተመለከተ ተጠሪ ከመነሻው ክስ በሚያቀርብበት ጊዜ የጠፋ ንብረት ዝርዝር ዋጋ አይነት እና ብዛት በመዘርዘር በቀረበው መሰረት በማስረጃ ያስረዳ ሲሆን አመልካች ያላስተባበለ ስለሆነ በስር ፍርድ ቤት አመልካችን አላፊ በማድረግ የንብረቱን ግምት እንዲከፍል የተሰጠ ውሳኔ በአግባቡ ስለሆነ እንዲያፀናልን የሚል ነው፡፡

አመልካች የመልስ መልሱን በ 17/12/2016 ዓ.ም በ 04 ገፅ የሰበር ቅሬታውን በማጠናከር አቅርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ በተገለፀው መሰረት የተጠቃለለ በመሆኑ እኛም ለሰበር ቅሬታ መነሻ የሆነውን ፍርድ፣ በግራ ቀኙ በኩል ከቀረበው ክርክር፣ ከማስቀረቢያ ነጥብ አንፃር በስር ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ አላፊነት አለበት ተብሎ የጠፋ ንብረት ግምት እንዲከፍል መወሰኑ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን በጭብጥነት በመያዝ አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች እና የሰበር ውሳኔዎች ጋር አገናዝበን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

መርምረን እንደተረዳነው ከሆነ የተጠሪ ዳኝነት ጥያቄ አመልካች የመደባቸው ጥበቃ ሰራተኞች ጉድለት በግቢ ውስጥ ያሉትን ንብረቶች በተለያዩ ጊዜያት የተሰረቁ ስለሆነ ስለሆነ በውላቸው መሰረት የተሰረቁ ንብረቶች ግምት እንዲተካ በማለት የጠየቀ ሲሆን አመልካች በመካከላቸው የጥበቃ አገልግሎት ውል መኖራቸውን በማመን ኃላፊነቱ በግቢ ውስጥ ያለው ንብረት ሳይሆን በመጋዘን ውስጥ ያለው ንብረት የመጋዘን ቁልፍ ተሰብሮ ሲሰረቅ እንደሆነ በግቢ ውስጥ ያሉ ንብረትም ቢሆን ተቆጥሮ ያልተሰጠ ስለሆነ የመክፈል ኃላፊነት የለብኝም በማለት ተከራክሯል፡፡

በአመልካችና ተጠሪ መካከል የጥበቃ አገልግሎት ውል በፅሁፍ የተደረገ ውል በማስረጃነት ለፍርድ ቤት ቀርቧል፡፡ በውላቸው አንቀፅ 3.2 ስር ከድርጅቱ መጋዘን ውጭ በየበረንዳው እና በየዛፉ ስር የተከማቹ የተለያዩ የፋብሪካ ምርቶች በግቢ ውስጥ ለግንባታ የመጡ ጥሬ እቃዎች በድርጅቱ አጥር ዙሪያ የተዘረጉ የመብራት ገመዶችን፣ የመኖሪያ መንደሮችን ጨምሮ አጠቃላይ በድርጅቱ ይዞታ ያሉ ንብረቶችን የመጠበቅ ግዴታ እንዳለበት ስለሚደነግግ አመልካች ከመጋዘን ውጪ ያሉትን ንብረቶች ተጠሪ ቆጥሮ ያስረከበ ስለመሆኑ በማስረጃ አላስረዳም በማለት የሚያነሳው ክርክር የማስረጃ ምዘና ስለሚሆን ይህ ችሎት ማስረጃ የመመርመርና የመመዘን ስልጣን የለውም፡፡

የዚህ ሰበር ችሎት ስልጣን የመጨረሻ ውሳኔ በተሰጠ ፍርድ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት ላይ ብቻ እንደሆነ የኢፌዴሪ ህገመንግስት አንቀፅ 80(3)(ሀ) እና የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 10(1) ስር በግልፅ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ከመሰረታዊ ማስረጃ ምዘና መርህ አንፃር ሲታይ ተጠሪ የጠፋው ንብረትን ዘርዝሮ እና እያንዳንዱ ንብረት የተገዛበት የዋጋ ዝርዝር ንብረቱ ስለመጥፋቱ በባለሞያ የተረጋገጠ ሰነድ ማስረጃ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተረጋግጦ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አሻሽሎ የወሰነ መሆኑን መዝገቡ ያስረዳል፡፡ አመልካች ከተጠሪ በኩል የቀረበውን ፅሁፍ ማስረጃ የሚያስተባብል ሰነድ አልቀረበም፡፡

አመልካች የተጠሪ ንብረቶች በግቢ ውስጥ የሚገኙ በመጋዘን ውስጥ ሊገቡ የማይችሉ ንብረቶች እና በመጋዘን ውስጥ ያሉ ንብረቶችን በሙሉ ለመጠባበቅ ግዴታ ገብቶ ከመጋዘን ውጪ በግቢ ውስጥ ያሉ ንብረቶች ስለመጥፋቱ ተጠሪ በተለያዩ ጊዜ በፅሁፍ ቢያሳውቅም አመልካች ግዴታውን ሊወጣ ባለመቻሉ የጠፉ የንብረት ዝርዝር እና ዋጋ የሚገልፅ ሰነድ ማስረጃ በማያያዝ ክስ አቅርቦ የስር ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በቀረበው ሰነድ ማስረጃ መሰረት የሰጠው ፍርድ የሚነቀፍ ባለመሆኑ ከማስረጃ ምዘና መርህም ሆነ ከህግ ረገድ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አላገኘንም፡፡

ሲጠቃለል አመልካች የተጠሪ ድርጅት ቅጥር ግቢ ከድርጅቱ መጋዘን ውጪ በየበረንዳውና በየዛፉ ስር የተከማቹ ንብረቶችን ለመጠበቅ ግዴታ ገብቶ በገባው ግዴታ መሰረት ባልመጠበቁ በግቢው ውስጥ ያሉ ንብረቶችን የጠፉ ስለመሆናቸው የሚያስረዳ ሰነድ ማስረጃ በማቅረቡ ስር ፍርድ ቤት ለጠፋው ንብረት አመልካችን ኃላፊ በማድረግ የንብረቱን ግምት እንዲከፍል ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተሸሽሎ የተሰጠው ፍርድ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያልተገኘ በመሆኑ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. የሲዳማ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 04346 በቀን 15/09/2015 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ አመልካች የጠቀሷቸው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጧቸው ሰበር መዝገብ ቁጥር 103910፣ 69915 እና ሰበር መዝገብ ቁጥር 797994 አስገዳጅ የህግ ትርጉምን የሚጣረስ ስላልሆነ እና መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያልተፀመበት በመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስነ ስርአት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9(1)(ሀ) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻቻሉ፡፡
4. በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠ እግድ ካለ ተነስቷል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

የሰ/መ/ቁ 253517

ታህሳስ 24 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ብርቅነሽ እሱባለው

ሀብታሙ እርቅይሁን

**አመልካች** - አቶ ጂወይድ ሰይድ ሳሊም - ጠበቃ ሽፈራው በላይ

**ተጠሪዎች፡ -**

1. አቶ አብዱልዋሲ አህመድ ኢብራሂም - ተወካይ አቶ ሰይፈዲን ቀርበዋል
2. የድሬዳዋ አስተዳደር የመሬት ልማት ማኔጅመትን ቢሮ - ነ/ፈጅ ጀማል ይብራሂም -ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረዉ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች በተጠሪዎች ላይ ያቀረቡትን ክስ መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡ አመልካች ለፍርድ ቤቱ ያቀረቡት ክስ ይዘትም በአጭሩ ታህሳስ 10 ቀን 2008 ዓ.ም በተደረገ የሊዝ ዉል መሠረት የፕላስቲክ ፋብሪካ እና የአስተዳደር ሕንፃዎችን በአጠቃላይ በ10,000,000.00 ብር የሚገመት ግንባታ አጠናቅቄ የፕላስቲክ ባግ ማምረቻ ማሽኖችን ወደ አገር ለማስገባት ስሞክር መንግስት በሚከተለዉ አረንጓዴ ፖሊሲ ልማት ምክንያት በመከልከሌ ህንፃዉን ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ ሳከራየሁ ቆይቻለሁ፤ በዚህም መሠረት ለ1ኛ ተጠሪ ከነሐሴ 11 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ነሐሴ ወር 2014 ዓ.ም በወር 20,000.00 ኪራይ እየከፈሉ ሲሰሩበት ቆይተዋል፡፡ ይሁንና 2ኛ ተጠሪ ከመመሪያ ዉጪ ፋብሪካዉን አልከፍትም በሚል ያለማስጠንቀቂያ ካርታዬን በመሰረዝ ያለምንም ጨረታ ለ1ኛ ተጠሪ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የሰጠዉ በመሆኑ 1ኛ ተጠሪ ከመስከረም 2013 ዓ.ም ጀምሮ ያለዉን

የኪራይ ገንዘብ እንዲከፍሉ እና ይዞታዉን እንዲያስረክቡኝ እንዲሁም ካርታዉ እንዲመክን ወይም ይህ ቢታለፍ የህንፃዉ ግምት በባለሙያ ተገምቶ የሚመጣዉን ብር 10,000,000.00 እንዲከፈለኝ ይወሰንልኝ የሚል ነዉ፡፡

1ኛ ተጠሪ ለክሱ በሰጠዉ መልስ አመልካች ለክርክሩ መነሻ በሆነዉ ይዞታ ላይ የፕላስቲክ ፋብሪካ ለመገንባት በ1993 ዓ.ም በተደረገ ዉል ከ2ኛ ተጠሪ የተረከበ ቢሆንም በዉሉ መሠረት ለመፈጸም ባለመቻሉ በቁጥር ድሬ26/1/21/96 ሐምሌ 12 ቀን 1996 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ አመልካች ካርታዉን እንዲያስረክቡ ማሳወቁን ተከትሎ አመልካች ለሊዝ ቦርድ ቅሬታ በማቅረቡ አመልካች በሦስት ወራት ዉስጥ ግንባታዉን አጠናቀዉ ወደ ስራ ካልገቡ ይዞታዉን የሚረከብ ስለመሆኑ አመልካች ጥቅምት 14 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ የከተማ አስተዳደሩ ያሳወቁ ቢሆንም በተደረገ የዳሰሳ ጥናት አመልካች ባለፉት 20 ዓመታት ይዞታዉን ለወሰዱበት ዓላማ ያላዋሉ እና ወደ ስራዉም ያልገቡ በመሆኑ የካቲት 15 ቀን 2012 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ካርታዉን ያመከነ ሲሆን አመልካች ቅሬታቸዉን ለከተማ አስተዳደሩ ካቢኔ አቅርበዉ ካቢነዉም አመልካች ይዞታዉን ለተፈለገዉ ዓላማ ሳያዉሉ ባልተገባ መንገድ በማከራየት ጥቅም እያገኙ መሆኑን በማረጋገጥ 2ኛ ተጠሪ የሰጠዉን ዉሳኔ አጽድቋል፡፡ አመልካች ለፕላስቲክ ማምረቻ የሚሆን ማሽን ገዝተዉ አገር ዉስጥ እንዳያስገቡ የተከለከሉ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ አላቀረቡም፡፡ አመልካች አንድ መጋዘን እንኳን በአግባቡ አልገነቡም፡፡ ካርታዉ ለ1ኛ ተጠሪ የተሰጠዉ በህግ አግባብ ብር 2,779,088.00 ካሳ በመክፈል በመሆኑ እና በመካከላቸዉ የተደረገ የኪራይ ዉልም ባለመኖሩ አመልካች ቦታዉን ለመረከብ፣ ካርታዉም እንዲመክን እና የኪራይ ገንዘብ እንዲከፈል ያቀረቡት ዳኝነት ተቀባይነት የለዉም፡፡ በይዞታዉ ላይ ሰፍሮ የነበረዉ ህንፃም ብር 10,000,000.00 እንደማያወጣ ጠቅሶ ባጠቃላይ የአመልካች ክስ ዉድቅ እንዲሆን ተከራክረዋል፡፡ 2ኛ ተጠሪም ባቀረበዉ መልስ 1ኛ ተጠሪ ካቀረበዉ መልስ ጋር ተመሳሳይ ይዘት ያለዉ ክርክር አቅርቧል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር እና ማስረጃ እንዲሁም ከሚመለከተዉ አካል ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ በማድረግ መርምሮ ከአመልካች ጋር የተደረገዉ የሊዝ ዉል ተቋርጦ ተሰጥቶአቸዉ የነበረዉ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ሊሰረዝ የቻለዉ አመልካች በሊዝ ዉሉ እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 25(2) ላይ በተደነገገዉ አግባብ ይዞታዉን በተገቢዉ ጊዜ ለተፈለገዉ ዓላማ ያላዋለዉ በመሆኑ ምክንያት መሆኑ መረጋገጡን፣ 2ኛ ተጠሪ ከአመልካች ጋር አድርጎት የነበረዉን የሊዝ ዉል በዚህ ሁኔታ አቋርጦ አመልካች በይዞታዉ ላይ የነበረዉን መብት ቀሪ ካደረገ በኋላ ይዞታዉን ለ1ኛ ተጠሪ በምደባ መስጠቱ የሊዝ አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 12 ድንጋጌን የተከተለ መሆኑን፣ የይዞታዉ ባለቤትነት ከአመልካች ወደ 1ኛ ተጠሪ የተላለፈዉም በህግ አግባብ በመሆኑ ተጠሪዎች በአመልካች የተጠየቀዉን ክፍያ የሚከፍሉበት ምክንያት የለም በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ዉሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም የከፍተኛ ፍርድ ቤቱን ዉሳኔ አጽንቶታል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም በዚሁ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካች መስከረም 18 ቀን 2016 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚሉባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር ታርሞ ይወሰንላቸዉ ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የሰበር አቤቱታቸዉ ይዘትም በአጭሩ 2ኛ ተጠሪ የሊዝ አዋጁን ማቋረጡ ተገቢ ነዉ ቢባል እንኳ በሊዝ አዋጁ አንቀጽ 23(6) ላይ በተመለከተዉ መሠረት ንብረቱን እንዳነሳ 2ኛ ተጠሪ የስድስት ወር

ጊዜ ሳይሰጠኝና በዚህም ምክንያት ተገቢዉን ቅሬታ ለማቅረብም ሆነ ንብረቴን ለማንሳት እድል አላገኘሁም፡፡ በሊዝ አዋጁ አንቀጽ 12 መሠረት የከተማ ቦታ ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች በምደባ መስጠት የሚቻል ቢሆንም ሌላ ሰዉ ግንባታ ያከናወነበት ይዞታ የሊዝ ዉል ተቋርጦም ቢሆን በምደባ ለሌላ ሰዉ በዘፈቀደ እንዲሰጥ የሚፈቅድ ህግ የለም፡፡ በይዞታዉ ላይ አመልካች የገነባሁት ግንባታ ፕላኑን የማይቃረንና በተሰጠኝ ህጋዊ የግንባታ ፈቃድ የተገነባ በመሆኑ ግንባታዉን ለተመሳሳይ ዓላማ መጠቀም ለሚፈልጉ ሰዎች 2ኛ ተጠሪ ጨረታ አወጥቶ በተገቢዉ ዋጋ ንብረቱን በመሸጥ ቀሪዉን ገንዘብ ለአመልካች መመለስ ሲገባዉ ከህግና መመሪያ ዉጪ በአሁኑ ወቅት እጅግ ከፍተኛ ዋጋ የሚያወጣዉን ንብረቴን በ2.7 ሚሊዮን ብር ካሳ እንድለቅ መወሰኑ ተገቢ አለመሆኑን ጠቅሼ በባለሙያ ተገምቶ ተጠሪዎች ግምቱን እንዲከፍሉኝ የጠየቅኩት ዳኝነት ዉድቅ መደረጉ ህጋዊ አይደለም፡፡ 1ኛ ተጠሪ በኪራይ ዉሉ መሠረት የቤቱን ኪራይ መክፈል ካቆመበት ጀምሮ ኪራዩን እንዲከፍል የጠየቅኩት ዳኝነትም ተገቢ አይደለም የሚል ነዉ፡፡

የሰበር አቤቱታዉ ተመርምሮም 2ኛ ተጠሪ የአመልካችን የሊዝ ዉል ለማቋረጥ በይዞታዉ ላይ የነበረዉን መጋዘንና ሌሎች የቢሮ ግንባታዎችን ስለማስተላለፍ በተመለከተ የቀረበዉን አቤቱታ በማለፍ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ዉሳኔ አግባብነት ግራ ቀኝ በተገኙበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል ተብሏል፡፡ በዚህም መሠረት ተጠሪዎች በተደረገላቸዉ ጥሪ መሠረት መልስ ሰጥተዋል፡፡ በዚህም መሠረት 1ኛ ተጠሪ ሰኔ 05 ቀን 2016 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች ወደ ስራዉ እንዲገቡ 2ኛ ተጠሪ ማስጠንቀቂያ ከመስጠት አልፎ ዉሉ ሲቋረጥ እና የይዞታ ማረጋገጫ እንዲመልሱ ሲጠየቁ ቀርበዉ ለመመለስ ፈቃደኛ ባልሆኑበት ሁኔታ ንብረት እንዳላነሳ ማስጠንቀቂያ አልተሰጠኝም በማለት ያቀረቡት መከራከሪያ ተቀባይነት ያለዉ አይደለም፡፡ በአዋጁ ላይ እንደተመለከተዉ ማስጠንቀቂያ የመስጠት ዓላማ በራስ ወጪ ንብረትን ለማንሳት ከመሆኑ አኳያ የማስጠንቀቂያ ስርዓት አልተፈጸመም ቢባል እንኳ በአዋጁ አንቀጽ 27(7) ላይ የተመለከተዉን ዉጤት የሚቀይር አይደለም፡፡ በአጠቃላይ አመልካች በሊዝ ዉሉ መሠረት የተረከበዉን ይዞታ በተገቢዉ ጊዜ ለተገቢዉ ዓላማ ማዋል ባለመቻላቸዉ ካርታዉ መክኖ ይዞታዉን ተረክቦ ለማልማት ከተወዳደሩት 76 አልሚዎች ዉስጥ 1ኛ ተጠሪ ተመርጠዉ በምደባ የተሰጣቸዉ እና ይህም በህግ አግባብ መሆኑን፣ በይዞታዉ ላይ ለነበረዉ ንብረትም ተገቢዉ ካሳ የተከፈለ መሆኑን ጠቅሰዉ ተከራክረዋል፡፡ 2ኛ ተጠሪም ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ይዘት ያለዉ ክርክር አቅርበዋል፡፡ አመልካች ሰኔ 21 ቀን 2016 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸዉን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉን ዉሳኔ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደሚቻለዉ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ለጠየቁት ዳኝነት መሠረት ያደረጉት 2ኛ ተጠሪ የሊዝ ዉሉን ያላግባብ በማቋረጥ በዉሉ መሠረት በእጃቸዉ ገብቶ የነበረዉን ካርታ ያላግባብ በማምከን በይዞታዉ ላይ ያለዉን መጋዘን በኪራይ ይዘዉ ለነበሩት 1ኛ ተጠሪ ይዞታዉን አሳልፎ መስጠቱን ሲሆን፣ ተጠሪዎች በበኩላቸዉ አመልካች በዉሉ በተመለከተዉ ጊዜ እና ሁኔታ ይዞታዉን ለተፈለገዉ ዓላማ ባለማዋላቸዉ ምክንያት የሊዝ ዉሉ ተቋርጦ በይዞታዉ ላይ ሰፍሮ ለሚገኝ ንብረት ለአመልካች ካሳ ተከፍሎ ይዞታዉ በህግ አግባብ ለ1ኛ ተጠሪ መተላለፉን በመግለጽ የሚከራከሩ መሆኑን ነዉ፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንኑ የግራ ቀኝን ክርክር መሠረት ያደረገ ጭብጥ በመያዝ የቀረቡትን ማስረጃዎች እንዲሁም የፕላስቲክ ባግ ማምረቻ ማሽን

ወደ አገር ዉስጥ እንዳይገባ ክልከላ የተደረገበት መሆን አለመሆኑን አስመልክቶ የሚመለከተዉ አካል አጣርቶ እንዲልክለት ካደረገ በኋላ ማስረጃዎቹን መርምሯል፡፡ በዚህም መሰረት በአመልካች እና በ2ኛ ተጠሪ መካከል ጳጉሜ 02 ቀን 1993 ዓ.ም በተደረገ የሊዝ ዉል 5000 ካ/ሜትር ስፋት ያለዉን ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ይዞታ የፕላስቲክ ፋብሪካ እንዲገነቡ የተሰጣቸዉ ቢሆንም አመልካች ይዞታዉን ለታቀደለት ዓላማ ለማዋል ባለመቻላቸዉ የሊዝ ዉሉ ሐምሌ 12 ቀን 1996 ዓ.ም ተቋርጦ አመልካች ካርታዉን ተመላሽ በማድረግ በይዞታዉ ላይ ያላቸዉን ንብረት እንዲያነሱ የተወሰነ ቢሆንም በአመልካች ቅሬታ መነሻነት ጉዳዩን በተመለከተዉ የሊዝ ቦርድ ዉሳኔ መሠረት ታህሳስ 10 ቀን 1998 ዓ.ም በተደረገ የሊዝ ዉል አመልካች ይዞታዉን ለተመሳሳይ ዓላማ ለማዋል የተረከቡ ቢሆንም ለተፈለገዉ ዓላማ ባለማዋላቸዉ የሊዝ ዉሉ ተሰርዞ ካርታዉን እንዲያስረክቡ ከተወሰነ በኋላ በተጠሪዎች መካከል ነሐሴ 25 ቀን 2012 ዓ.ም በተደረገ የሊዝ ዉል ይዞታዉ ለተመሳሳይ ዓላማ ለ1ኛ ተጠሪ በምደባ እንደተሰጣቸዉ እንዲሁም አመልካች ጳጉሜ 01 ቀን 2009 ዓ.ም በተደረገ የኪራይ ዉል ለ1ኛ ተጠሪ በብር 20,000.00 በይዞታዉ ላይ ያረፈዉን መጋዘን አከራይተዉ የነበረ ስለመሆኑ መረጋገጡን፣ አመልካች የፕላስቲክ ባግ ማምረቻ ፋብሪካ ለመገንባት የሚያስፈልጉ መሣሪያዎችን ወደ አገር ዉስጥ እንዳያስገባ የተከለከለ ስለመሆኑ አለመረጋገጡን፣ በአመልካች እና በ2ኛ ተጠሪ መካከል ጳጉሜ 02 ቀን 1993 ዓ.ም የተደረገዉ የሊዝ ዉል ታህሳስ 10 ቀን 1998 ዓ.ም በተደረገ ዉል ተተክቷል ቢባል እንኳ አመልካች አስቀድሞም ይዞታዉ በእጃቸዉ የነበረ ከመሆኑ አኳያ በሊዝ ዉሉ ላይ በተመለከተዉ አግባብ በአራት ዓመት ከስድስት ወራት ዉስጥ ግንባታዉን አከናዉነዉ በማጠናቀቅ ለታለመለት ዓላማ ለማዋል ያለባቸዉን ግዴታ ባለመወጣታቸዉ የሊዝ ዉሉ ተቋርጦ ይዘዉት የነበረዉ ይዞታ ለ1ኛ ተጠሪ መሰጠቱን በፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ ይህ የፍሬ ነገር ድምዳሜ ጉዳዩን በይግባኝ በተመለከተዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80 (3/ሀ) ላይ እንዲሁም በፌዴራል ፍርድ ቤቶች በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4) እና አንቀጽ 10 ላይ እንደተመለከተዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት በማረም ላይ የተገደበ በመሆኑ የስር ሁለቱ ፍርድ ቤቶች ከላይ በተመለከተዉ ሁኔታ የደረሱበትን የፍሬ ነገር ድምዳሜ በድጋሚ መዝኖ ትክክለኛነታቸዉን የማረጋገጥ ስልጣን የለዉም፡፡

ማስረጃን መዝኖ ፍሬ ነገርን የማጣራት ስልጣን ባላቸዉ ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ አመልካች በሊዝ የወሰዱትን ይዞታ በተገቢዉ ጊዜ ለተገቢዉ ዓላማ አለማዋላቸዉ ከተረጋገጠ ዉጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ የሊዝ አዋጅ ቁጥር 721/2004 አኳያ መመርመሩ ተገቢ ነዉ፡፡ ማንኛዉም የሊዝ ዉል ባለይዞታ በአዋጁ እንዲሁም በሊዝ ዉሉ ላይ በተመለከተዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥ ግንባታዉን ማጠናቀቅ ያለበት ሲሆን፣ በዚህ ሁኔታ ያላጠናቀቀ እንደሆነ የሊዝ ዉሉ የተቋረጠበት ሰዉ ከስድስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ዉስጥ በቦታዉ ላይ የሰፈሩ ንብረቶችን እንዲያነሳ ማስጠንቀቂያ በመስጠት የሊዝ ዉሉን አቋርጦ ቦታዉን መልሶ መረከብ የሚችል ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 23(1)፣ 23(5) እና 23(6) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህም የሚያሳየዉ በሊዝ ዉሉ መሠረት ግንባታዉ ያልተጠናቀቀ እንደሆነ ዉሉ እንዲፈርስ ለፍርድ ቤት ዳኝነት መጠየቅ ሳያስፈልገዉ ስልጣን ያለዉ አካል በተናጥል ዉሉን የማቋረጥ መብት ያለዉ መሆኑን ነዉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በአዋጁ ላይ የተመለከተዉ ማስጠንቀቂያ የመስጠት አስፈላጊነት የሊዝ ዉሉ የተቋረጠበት ሰዉ በይዞታዉ ላይ የሰፈረዉን ግንባታ ማንሳት እንዲችል ለማሳሰብ ብቻ ስለመሆኑ ከድንጋጌዉ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም የሊዝ መብት የተሰጠዉ ሰዉ የሊዙን ዓላማ ባገናዘበ መልኩ በይዞታዉ ላይ ተገቢዉን ግንባታ በተገቢዉ ጊዜ ያላጠናቀቀ መሆኑ ከተረጋገጠ ስልጣን ያለዉ አካል የሊዝ ዉሉን ሲያቋርጥ ማስጠንቀቂያ

አለመስጠቱ ብቻዉን እርምጃዉን ህገ ወጥ አያደርገዉም፡፡ በተያዘዉም ጉዳይ፣ ከላይ እንደተገለጸዉ፣ አመልካች በሊዝ ዉሉ ግዴታ የገባዉ በቦታዉ ላይ የፕላስቲክ ፋብሪካ ለመገንባት ቢሆንም ከ1993 ዓ.ም ጀምሮ 2ኛ ተጠሪ የይዞታ ካርታዉን ሰርዞ ይዞታዉን ለ1ኛ ተጠሪ እስካስረከበበት 2012 ዓ.ም ድረስ ይዞታዉን ለታቀደለት ዓላማ ያላዋሉ ስለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ 2ኛ ተጠሪ የሊዝ ዉሉን ከማቋረጡ በፊት ለአመልካች ማስጠንቀቂያ አለመስጠቱ ብቻዉን እርምጃዉን ህገ ወጥ አያሰኘዉም፡፡ የሊዙ ዓላማ ለማኑፋክቸሪንግ ስራ ከመሆኑ አኳያ 2ኛ ተጠሪ ከአመልካች ጋር የነበረዉን የሊዝ ዉል በዚህ አግባብ አቋርጦ መብቱን ለ1ኛ ተጠሪ በምደባ መስጠቱ የአዋጁን አንቀጽ 12(1-ሠ) ድንጋጌን መሠረት ያደረገ ከመሆኑም በላይ 2ኛ ተጠሪ ይዞታዉን ለ1ኛ ተጠሪ የሰጠበት አግባብ ተገቢ መሆን አለመሆኑ ከአመልካች መብት አንፃር የሚያመጣዉ ለዉጥ ባለመኖሩ አመልካች ይህን አስመልክቶ የሚያቀርበዉ ክርክር ተቀባይነት የለዉም፡፡

በሌላም በኩል አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ከጠየቋቸዉ ዳኝነቶች ዉስጥ አንዱ በይዞታዉ ላይ ለሰፈረዉ ንብረት ዋጋዉ ይከፈለኝ የሚል ነዉ፡፡ የሊዝ ዉሉ በህግ አግባብ በመቋረጡ ምክንያት ይዞታዉን እንዲያስረክብ የተደረገ ሰዉ በይዞታዉ ላይ ያስፈረዉን ንብረት ካላነሳ ሁለት ዉጤቶች እንደሚያስከትል የአዋጁ አንቀጽ 23(7-8) ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ አንደኛዉ ዉጤቱ፣ ከላይ እንደተገለጸዉ፣ ይዞታዉን እንዲለቅ የተደረገ ሰዉ ንብረቱን የማንሳት መብት ያለዉ ሲሆን፣ ሁለተኛዉ ግንባታዉ በፕላኑ መሠረት የተገነባ መሆኑ ከተረጋገጠ ስልጣን ያለዉ አካል ንብረቱን በግልጽ ጨረታ ሸጦ ሽያጩን ለማስፈጸም የወጡ ወጪዎችን ቀንሶ ተራፊ ገንዘብ ካለ ለባለመብቱ ተመላሽ ማድረግ ነዉ፡፡ አመልካች በይዞታዉ ገንብቻለሁ የሚሉት ቤት ከፕላኑ ዉጪ ነዉ የሚል ክርክር ተጠሪዎች አላነሱም፡፡ ይዞታዉ ለአመልካች ተሰጥቶ የነበረዉ ለፕላስትክ ፋብሪካ ስራ ሲሆን፣ የሊዝ ዉሉ ከተቋረጠ በኋላ ለ1ኛ ተጠሪ የተላለፈዉም ለዚሁ ዓላማ ስለመሆኑ እንዲሁም 1ኛ ተጠሪ ይዞታዉን የተረከበዉ አመልካች በላዩ ላይ ከገነባቸዉ ቤቶች ጋር ስለመሆኑም አላከራከረም፡፡ ይሁንና 2ኛ ተጠሪ ተገቢዉን ማስጠንቀቂያ ሳይሰጥ የሊዝ ዉሉን አቋርጦ ይዞታዉን በላዩ ላይ ከሰፈረዉ ንብረት ጋር ለ1ኛ ተጠሪ በማስተላለፉ አመልካች ንብረቱን ለማንሳት ባለዉ መብት እንዳይጠቀም፣ ከዚህም አልፎ 2ኛ ተጠሪ ይዞታዉ በላዩ ላይ ከሰፈረዉ ንብረት ጋር ለ1ኛ ተጠሪ ያስተላለፈዉ ያለ ጨረታ በመሆኑ ንብረቱ በትክክለኛ የገበያ ዋጋ ቢሸጥ ኖሮ አመልካች ማግኘት ይችል የነበረዉን የንብረቱን ግምት አመልካች እንዳያገኙ ምክንያት ሆኗል፡፡ በርግጥ በይዞታዉ ላይ ላለዉ የአመልካች ንብረት ግምቱ በካሳ መልክ ለአመልካች ሊከፈለዉ እንደሚገባ ታምኖበት ብር 2,779,088.00 ለአመልካች እንዲከፈል በ2ኛ ተጠሪ ተወስኗል፡፡ ይሁንና አመልካች ዳኝነት የጠየቁት የንብረቱ ግምት ብር 10,000,000.00 መሆኑን በመጥቀስ ነዉ፡፡ ነገር ግን ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይዞታዉ በህግ አግባብ ለ1ኛ ተጠሪ የተላለፈ መሆኑን ጠቅሶ በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረበዉን ዳኝነት ዉድቅ አድርጎታል፡፡ ነገር ግን ይዞታዉ በህግ አግባብ ለ1ኛ ተጠሪ መተላለፉ አመልካች በንብረቱ ላይ የሚገባዉን ካሳ እንዳያገኝ ምክንያት ሊሆን አይችልም፡፡ በመሆኑም የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይዞታዉ ላይ የሰፈረዉ ንብረት ዓይነት እና ግምቱን አጣርቶ ዉሳኔ መስጠት ሲገባዉ ከላይ የተመለከተዉን ምክንያት በመጥቀስ ዉድቅ ማድረጉ ሊታረም የሚገባዉ ነዉ፡፡

በሌላ በኩል ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ከካሳ ጋር በተያያዘ አመልካች ያቀረቡትን ቅሬታ መርምሮ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ በቀረበዉ ዳኝነት ላይ ተገቢዉን ዉሳኔ ሳይሰጥ ማለፉ ተገቢ አለመሆኑን ጠቅሶ፤ በሌላ በኩል በይዞታዉ ላይ ያሉ ቤቶች መጋዘን፣

ማሳ ታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ለአስተዳደር የሚዉሉ ቢሮዎች፣ የሠራተኞችን ማረፊያ እና የመጸዳጃ ቤቶች ሲሆኑ ለእነዚህ ግንባታዎች የወጣዉን ወጪ ብር 936,361.04 እንደሆኑ ተጠቅሶ በተጠሪዎች የቀረበዉን ግምት አመልካች አለማስተባበሉንና ግንባታዉ በተከናወነበት እና የሊዝ ዉሉ በተቋረጠበት ጊዜ ያለዉን የግንባታ ዋጋ ልዩነት ከግምት ገብቶ ለአመልካች ብር 2,779,088.00 እንዲከፈል መወሰኑን የዉሳኔዉ ግልባጭ ያሳያል። ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ለዚህ ዉሳኔዉ መሠረት ያደረገዉ ለአመልካች ሊከፈለዉ የሚገባዉ በይዞታዉ ላይ የሚገኙትን ቤቶች ለመስራት የሚወጣዉን ወጪ ከግምት ዉስጥ በማስገባት እንጂ የንብረቱን የገበያ ዋጋ አለመሆኑ መገንዘብ ይቻላል። ይህ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ድምዳሜ በሊዝ በተሰጠ ቦታ ላይ የሰፈረ ንብረት የሊዝ ዉል መቋረጡን ተከትሎ ከይዞታዉ ጭምር ለሌላ ሰዉ ሲተላለፍ የሚሸጠዉ በጨረታ በገበያ ዋጋ ስለመሆኑ የሚደነግገዉን የአዋጁን አንቀጽ 23(7 እና 8) ላይ የተመለከተዉን ድንጋጌ ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተነዋል። ይልቁንም በዚህ ድንጋጌ መሠረት ለአመልካች መወሰን የሚገባዉ የግንባታ ወጪ (book value) ሳይሆን፣ ለክርክሩ መነሻ በሆነዉ ይዞታ ላይ የሰፈሩ መሆናቸዉ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዉሳኔ የተዘረዘሩት ቤቶች የሊዝ ዉሉ ተቋርጦ ይዞታዉ ወደ 1ኛ ተጠሪ እንዲተላለፍ በተደረገበት ወቅት ማለትም የካቲት 16 ቀን 2012 ዓ.ም የነበራቸዉ የገበያ ዋጋ (market value) ሊሆን ይገባል። ለአመልካች በካሳ መልክ እንዲከፈል በ2ኛ ተጠሪ የተወሰነዉ ብር 2,779,088.00 የሊዝ ዉሉ በተቋረጠበት ወቅት የነበረዉ የቤቱ የገበያ ዋጋ? ወይስ የግንባታ ወጪ? የሚለዉ ግልጽ አይደለም። ከላይ እንደተገለጸዉ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ይህን አስመልክቶ አመልካች ያቀረቡትን ዳኝነት ስላልመረመ ይህን አስመልክቶ በፍሬ ነገር ደረጃ ያልለዩ ሲሆን፣ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በ2ኛ ተጠሪ እንዲከፈል የተወሰነዉ የካሳ መጠን ቤቱ በተገነባበት ወቅት ለግንባታ የወጣ ወጪ ነዉ በሚል ከቀረበዉ ብር 936,361.04 ዉሉ በተቋረጠበት ወቅት ሊወጣ ከሚችል የግንባታ ወጪ አንፃር በማነፃፀር ወሰነ እንጂ ይህን የፍሬ ነገር አልለየም። በመሆኑም፡-

1. *ለአመልካች በካሳ መልክ ብር 2,779,088.00 እንዲከፈል 2ኛ ተጠሪ ሲወስን መሠረት ያደረገዉ የሊዝ ዉሉ በተቋረጠበት ወቅት ቤቱን ለመገንባት የወጣዉን ወጪ ነዉ? ወይስ የቤቶቹን የገበያ ዋጋ ነዉ?*

2. *2ኛ ተጠሪ ለዉሳኔዉ መሰረት ያደረገዉ ዉሉ በተቋረጠበት ወቅት የነበረዉን የቤቶቹን የገበያ ዋጋ ከሆነ አገማመቱ በተገቢ ባለሙያዎች በአግባቡ የተከናወነ ነዉ? ወይስ አይደለም?*

3. *ግምቱ የቤቶቹን የገበያ ዋጋ መሠረት ያላደረገ ከሆነ፣ ዉሉ ተቋርጦ አመልካች ይዞታዉን እንዲለቁ በተወሰነበት የካቲት 16 ቀን 2012 ዓ.ም ለክርክሩ መነሻ በሆነዉ ይዞታ ላይ የሚገኙትና በአመልካች የተገነቡት ቤቶች የገበያ ዋጋ ስንት ነዉ? የሚሉት ጭብጦች በአግባቡ ተጣርተዉ እልባት ሊያገኙ የሚገባቸዉ ናቸዉ።*

ሌላዉ የአመልካች ክርክር 1ኛ ተጠሪ የቤቱን ኪራይ እንዲከፍል የተጠየቀዉ ዳኝነት ሳይወሰን የመታለፉን አግባብነት የሚመለከት ነዉ። ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደሚቻለዉ 1ኛ ተጠሪ በመካከላቸዉ ባለዉ የኪራይ ዉል መሠረት ከመስከረም 2013 ዓ.ም ጀምሮ ያለዉን የኪራይ ዉል እንዲከፍል ዳኝነት መጠየቁን ሲሆን፣ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ይህን አስመልክቶ የቀረበዉን ዳኝነት ዉድቅ ያደረገዉ የሊዝ ዉሉ ተቋርጦ ወደ 1ኛ ተጠሪ የተላለፈዉ በህግ አግባብ መሆኑ መረጋገጡን በመጥቀስ ነዉ። ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ይህን አስመልክቶ ያለዉ ነገር የለም። በሌላም በኩል ከአመልካች ጋር የነበረዉ የሊዝ ዉል ተቋርጦ ይዞታዉ ለ1ኛ ተጠሪ የተላለፈዉ ነሐሴ 2012 ዓ.ም ስለመሆኑ ተረጋግጧል። በመሆኑም ከመስከረም 2013 ዓ.ም ጀምሮ

ያለዉን የኪራይ ገንዘብ 1ኛ ተጠሪ እንዲከፍሉት አመልካች የሚያቀርቡት ዳኝነት ተቀባይነት ያለዉ ባለመሆኑ በዚህ ረገድ ያቀረቡትን ቅሬታ ችሎቱ አልተቀበለዉም፡፡

በአጠቃላይ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ይዞታ አስመልክቶ ከአመልካች ጋር ተደርጎ የነበረዉ ዉል ተቋርጦ ወደ 1ኛ ተጠሪ የተላለፈዉ በህግ አግባብ ነዉ በሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረቡትን ክርክር ዉድቅ በማድረግ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በጸናዉ ዉሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም፤ ይሁንና በይዞታዉ ላይ የሰፈረዉን ንብረት አስመልክቶ አመልካች ያቀረቡትን የካሳ ጥያቄ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ያለ በቂ ምክንያት ዉድቅ ማድረጉ እንዲሁም ከንብረቱ ጋር በተያያዘ ለአመልካች ሊከፈል የሚገባዉ ክፍያ የንብረቱ የገበያ ዋጋ ሆኖ ለአመልካች እንዲከፈል በ2ኛ ተጠሪ የተወሰነዉ የገንዘብ መጠን ግምቱ የንብረቱን የገበያ ዋጋ መሆን አለመሆኑንና ከፍ ሲል በተመለከተዉ መልኩ በህግ አግባብ በባለሙያ ተገምቶ የቀረበ መሆን አለመሆኑ አጣርቶ መወሰን ሲገባዉ ይህን ሳያደርግ የሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያትም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ዉሳኔ**

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 17652 ላይ ሰኔ 17 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 232885 ላይ ሰኔ 27 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጡት ዉሳኔ በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1) መሠረት ተሻሽለዋል፡፡

2. ለክርክሩ መነሻ በሆነዉ ይዞታ ላይ ካረፈዉ ንብረት ጋር በተያያዘ የተጠየቀዉን ግምት (ካሳ) አስመልክቶ በሁለቱም ፍርድ ቤቶች የተሰጠዉ የዉሳኔ ክፍል ተሽረዋል፤ ቀሪዉ የዉሳኔዉ ክፍል ጸንተዋል፡፡

3. ለክርክሩ መነሻ በሆነዉ ይዞታ ላይ አመልካች የገነባቸዉን ቤቶች አስመልክቶ ሊከፈላቸዉ የሚገባዉ ካሳ ንብረቱ ለ1ኛ ተጠሪ በተላለፈበት ወቅት በነበረዉ የገበያ ዋጋ ግምት እንጂ ቤቶቹን ለመገንባት የወጣዉን ወጪ መሠረት በማድረግ አይደለም ብለናል፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተዘግቶ የነበረዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ ከንብረቶቹ ጋር በተያያዘ ለአመልካች ሊከፈል የሚገባዉን ካሳ ከላይ በፍርድ ክፍል ከተመለከቱት ጭብጦች አንፃር መርምሮ ተገቢዉን በማጣራት ለአመልካች ሊከፈል የሚገባዉ የካሳ መጠን 2ኛ ተጠሪ እንዲከፈለዉ ከወሰነዉ ብር 2,779,088.00 በላይ መሆን አለመሆኑን በማጣራት፣ ግምቱ ከዚህ የገንዘብ መጠን በላይ ከሆነ ልዩነቱ ለአመልካች እንዲከፈል በማድረግ ተገቢዉን እንዲወስን ጉዳዩ በሰበር መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(2) መሠረት ተመልሶለታል፡፡

4. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

**መ/ዐ**

**ማስታወሻ፡** - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

*የሰ/መ/ቁ 253704*
*ታህሳስ 24 ቀን 2017ዓ/ም*

**ዳኞች** ፡- ገበየሁ ፈለቀ

ደረጀ አያና

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

ብርሃኑ መንግሥቱ

አመልካች ፡- ወ/ሮ አገሪቱ በዛ

ተጠሪ፡- አቶ በላይ በዛ

ይህ መዝገብ ከሰ/መ/ቁ/ 252811 ጋር ተጣምሮ ተመርምሮ የሚከተለዉ የፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ፡- ሟች ያደረጉት ኑዛዜ ተጠሪን ከውርስ የሚነቅል ነው በሚል የተሰጠው ውሳኔ በስር ፍ/ቤት በግልፅ ክርክር ሳይደረግበት በሰበር ደረጃ ታይቶ የመወሰኑን አግባብነት የሚመለከት ነዉ፡፡ክርክሩ በተጀመረበት በዳውንት ወረዳ ፍ/ቤት አመልካቾች ተከሳሽ ተጠሪ ደግሞ 1ኛ ከሳሽ ሙሉ በዛ ሁለተኛ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ በተጠሪ እና ሙሉ በዛ በተባሉ አሁን የክርክሩ አካል ያልሆኑ ሰዉ በአመልካቾች ላይ የቀረበዉ ክስ ይዘት የሰበር አመልካቾች እና ተጠሪዎች የአንድ አባት እና እናት ልጆች ስንሆን ሟች እናታችን አደሌ ገላዉ በህወት ሳለች በ2002 ዓ/ም በዳዉንት ወረዳ ፍትህ ጽ/ቤት ቀርባ የመሬት ይዞታዋን ተናዛልን ወራሽነታችንንም አስወስነናል የሰበር አመልካቾች ይዘዉ ስለሚገኙ ድርሻችንን እንዲያካፍሉን ይወሰንልን የሚል ነዉ፡፡ የሰበር አመልካቾች የሰጡት መልስ ይዘትም ክሱ በይርጋ ቀሪ ነዉ፡፡ ሟች እናታችን በ2002 ዓ/ም ለግራ ቀኛችን ያደረገችዉን ኑዛዜ በ2004 ዓ/ም አንስታ ለእኛ በኑዛዜ አስተላልፋለች ፡፡ በኑዛዜዉ መሰረትም ድርሻችንን ተካፍለን በድርሻችን ላይ ቤት ሰርተን እየኖርን የምንገኝ ስለሆነ

**ማስታወሻ፡** - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማ አያገለግልም!

የመናካፈላቸዉ የዉርስ ሀብት የለም የሚል ነዉ ። ጉዳዩ በዚህ መልክ የቀረበለት የዳዉንት ወረዳ ፍርድ ሟች እናታቸዉ በ2002 ዓ/ም ለተጠሪ ጭምር ተናዘዉ የነበረ ቢሆነም በ2004 ዓ/ም ለሰበር አመልካቾች የተናዘዙ ስለሆነ የ2002 ዓም ኑዛዜ ቀሪ ስለሆነ መብት ያላቸዉ የአሁን አመልካቾች ናቸዉ ሲል ወስኗል ።ተጠሪ በዉሳኔዉ ቅር ተሰኝተዉ ጉዳዩን በይግባኝ ለሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወረዳዉ ፍርድ ቤት ዉሳኔ ስህተት የለበትም በማለት ቅሬታዉን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 337 መሰረት ሰርዞታል።

ተጠሪ ቅሬታቸዉን ቀጥለዉ ለአማራ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ሰበር ሰሚ ችሎቱ የስር ፍርድ ቤቶቹን ዉሳኔ በመሻር የዳውንት ወረዳ የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ ሟች አደሌ ገላው በ2004 ዓ.ም ያደረገችውን ኑዛዜ በተመለከተ ኑዛዜውን በምታደርግበት ጊዜ ሙሉ ጤነኛ መሆን አለመሆኗን ከዚህም አንፃር ኑዛዜው ሊፀና ይገባል ወይስ አይገባም የሚለውን ጭብጥ በመመስረት እንደገና የግራ ቀኙን ምስክር በመስማት አስፈላጊ ከሆነም በኑዛዜው ላይ የነበሩ እማኞችን አስቀርቦ በመስማት የመሰለውን እንዲወስን ጉዳዩን ለዳዉንት ወረዳ ፍርድ ቤት መልሶታል።በዚህ መነሻነት የዳዉንት ወረዳ ፍርድ ተጨማሪ ምስክሮችን ከግራ ቀኙ በመስማት ሟች አዲሴ ገላው በ2004 ዓ.ም ኑዛዜውን ስታደርግ ማንኛውንም ህጋዊ ተግባር ለማድረግ በምትችልበት ሁኔታ ሙሉ ጤነኛ የነበረች እና ኑዛዜውም የህግ ፎርማሊቲ በጠበቀ መልኩ የተደረገ በመሆኑ ሊፈርስ የሚችልበት የህግ አግባብ ስለሌለ ሟች አደሌ ገላው ለአመልካቾች የተናዘዘችው ኑዛዜ ሊፀና ይገባል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል።

ተጠሪም በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ከፍተኛ ፍርድ ቤቱም የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን በፍ/ብ/ስ/ህ/ቁ 337 መሰረት በመሰረዝ ሳይቀበለዉ ቀርቷል። በመቀጠልም ተጠሪ ውሳኔውን ለማሳረም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ሰበር ሰሚ ችሎቱም ተጠሪ የሟች ልጅ መሆኗ ተረጋጧል።እንዲሁም ሟች በ2004 ዓ.ም ባደረገችው ኑዛዜ ለአመልካቾች ሙሉ መሬቷን ያስተላለፈች መሆኑ ተረጋግጧል።ከዚህም አንፃር የስር ፍ/ቤት ይህ ከውርስ መንቀል ነው ወይስ አይደለም ከሚለው ነጥብ ተመልክቶ ስለኑዛዜው ህጋዊነት ሳይወስን ማለፉ ተገቢ አይደለም በማለት ከውርስ መነቀል እና አለመነቀል የህግ ክርክር በመሆኑ በዚህ ሰበር ችሎት ታይቶ እልባት ሊሰጥበት የሚገባ ነጥብ ነዉ ብሎ ሟች አደሌ ገላው ያደረጉት ኑዛዜ ባላቸው የገጠር ይዞታ መሬቶች በሙሉ ላይ መሆኑ የኑዛዜው ይዘት ከማሳየቱም በላይ ኑዛዜው የሟችን የገጠር ይዞታ መሬቶች የሚያጠቃልል አይደለም የሚል ክርክር አልቀረበም።ስለሆነም የሟች ኑዛዜ ጠቅላላ ኑዛዜ ሊባል እንደሚችል ከፍ/ህ/ቁ/ 912/1 ድንጋጌ መረዳት ይቻላል።ይህ ከሆነ ደግሞ ተወላጇን ከውርስ የነቀለችበት ምክንያት ስለመኖሩ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር የለም።ለአካለ መጠን የደረሰን ተወላጅ ከገጠር መሬት ውርስ በዝምታ መንቀል የማይቻል ስለመሆኑ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 163896 አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰቶበታል።ስለሆነም የሟች አዲሴ ኑዛዜ ተጠሪን ያለምክንያት ከውርስ

የነቀለ ሆኖ ሳለ ህጋዊ ነው ተብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት ውሳኔውን ሽሮ የሚችን የውርስ የገጠር ይዞታ ለተጠሪ በድርሻ ልክ እኩል ሊካፈሉ ይገባል ሲል ወሳኔ አሳልፏል፡፡

አመልካቾች በየግላቸው ለዚሁ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታቸውን ያቀረቡት ከላይ በተጠቀሰው መንገድ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሟል በማለት ሲሆን ፍ/ቤቱም ሁለቱን መዝገቦች እንዲጣመሩ አድርጓቸዋል፡፡ የአቤቱታቸውም አጭር ይዘት፡-ተጠሪ በስር የወረዳ ፍርድ ቤት የሚችን የውርስ ንብረት ያካፍሉን በማለት የወራሽነት ክርክር ያቀረቡት ሚች በ2004 ዓ.ም ባደረጉት ኑዛዜ መሠረት ተከራካሪ ወገኖች ክርክር የቀረበበትን ንብረት ተከፋፍለን ይዘን ከቆየን ከ9 ዓመት በኃላ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1000 (1) መሰረት በሶስት አመት  ይርጋ ይታገዳል ብለን ያቀረብነዉ የይርጋ ክርክር የታለፈዉ ያላግባብ ነዉ፡፡ ስለዉርስ መነቀል አለመነቀል በስር ፍረድ ቤት ተነስቶ ክርክር ሳይደረግ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተነስቶ መወሰኑ ስህተት ነዉ የሚል  ነዉ፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም መዝገቡን መርምሮ ሚች በ2004 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ ከውርስ ነቅሎኛል የሚል ክርክር ጉዳዩን በመጀመርያ ደረጃ ስልጣኑ በተመለከተው የዳውንት ወረዳ ፍ/ቤት በተጠሪ መነሳት አለመነሳቱን ተነስቷል ከተባለም በሰበር ደረጃ ታይቶ መወሰኑ ከአመልካች ይግባኝ መብት አንፃር ያለው አንደምታ በስር የዳውንት ወረዳ ፍ/ቤት ኑዛዜ ከውርስ ነቅሎኛል የሚለው ክርክር ከተነሳ በሰበር ደረጃ የመመርመሩን ስነ-ስርዓታዊነት፤የይርጋ ክርክሩ በወረዳ ፍ/ቤት የታለፈበት አግባብ ከውርስ ህጉ፤ከፍብሄር ስነ-ስርዓት ህጉ፤ የሰበር ሰሚ ችሎቱ በሰበር መዝገብ ቁጥር 37762  ከሰጠው አስገዳጅ የሰበር ውሳኔ አንፃር ተጠሪ በተገኙበት ጉዳዩን ለመመርመር ያሥቀርባል ብሎ ግራ ቀኙ ክርክር አድርገዉበታል፡፡

ተጠሪም በሀምሌ 29 ቀን 2016 ዓ.ም ባቀረቡት መልስ፡-ሚች እናታችን በህይወት ሳለች ማንም ሳያስገድዳት በነፃ ፍላጎቷ ወዳና ፈቅዳ ስልጣን ባለው የመሬት አስተዳደር ፍ/ቤት ቀርባ እማኞች ባሉበት በግልፅ የኑዛዜ ስርዓት ቀድሞ በስራ ላይ በነበረው የመሬት አዋጅ ቁጥር 133/98 ደንብ ቁጥር 51/99 መሰረት የመሬት አዋጅ በሚፈቅደው መሰረት የተመን መሬቶቿን ለአመልካች እና ለተጠሪ በቀን 8/3/2002 ዓ.ም አስተላልፋለች::በዚህ መሰረት ግራቀኛችን እናታችን በህይወት ሳለች ጀምሮ በውርስ መሰረት ተከፋፍለን የየድርሻችንን ለይተን ይዘነው እንዳለ ይህ የመጀመሪያው ህጋዊ ኑዛዜ በህግ አግባብ ሳይሻር በ 2004 ዓ.ም በድጋሚ የተሰጠ ኑዛዜ በማቅረብ አመልካች አይመለከትህም ልባል አይገባም ፡፡ የመጀመሪያው ነዛዜ ሳይሻር ለሁለተኛ ጊዜ የተሰጠው ኑዛዜ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባውም፡፡በተሻሻለው የክልሉ የመሬት አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀፅ 55 ድንጋጌ መሰረት ቀደም ሲል የተላለፈልኝ የውርስ መሬት በመሆኑ ይህም ባለይዞታዋ በህይወት ሳለች የተሰጠ ኑዛዜ በመሆኑ የፍ/ስ/ብ/ ቁጥር 1000 (1) መሰረት በ 3 ዓመት ይርጋ ቀሪ ነው ሊባል አይገባውም፡፡እንዲሁም በፍትሀብሔር ህግ ቁጥር 1853(1) መሰረት በመካከላችን የቅርብ ዝምድና ስላለን ይርጋው የሚቋረጥ ስለሆነ በይርጋ ሊታገድ አይገባም፡፡አመልካች ያቀረበችው አዲስ የመሬት ኑዛዜ እኔን ተወላጅን ከውርስ የሚነቅለኝ ወይም ያገለለኝ በመሆኑ ኑዛዜው ተሰርዞልኝ የውርስ መሬቴን ታካፍለኝ

በማለት ነው ክርክሩ የተነሳው፡፡ በዚህ የኑዛዜ ሰነድ የመሬቱ ባለይዞታ ከውርስ ለመንቀል የደረሰችበትን ምክንያት በኑዛዜው ውስጥ ካልጠቀሰች ኑዛዜው በህግ የማይፀና መሆኑ ግልፅ ከመሆኑም በላይ በስር ፍ/ቤት በነበረኝ ክርክር ሰነዱ ከውርስ የነቀለኝ ነው፤ ኑዛዜው አመልካችን የሚጠቅም እኔን የሚጎዳ ነው ስለዚህ ይሰረዝልኝ በማለት ተከራክሬአለሁ ስለዚህ ክርክር አልተነሳም ሊባል አይችልም በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ስህተት የሌለበት ስለሆነ ሊጸና የሚገባዉ ነዉ የሚል ይዘት ያለዉ ክርክር አቅርበዋል፡፡

አመልካችም በቀን 14/12/2016ዓ.ም የተፃፈ የስር ክርክራቸዉን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ  የአጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ ተገለጸው ሲሆን እኛም የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን ያስቀርባል ሲበል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነዉም ቅሬታዉ ያስቀርባል ሲባል የተያዘዉ ጭብጥ ሟች በ2004 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ ከውርስ ነቅሎኛል የሚል ክርክር ጉዳዩን በመጀመርሪያ ደረጃ ስልጣን በተመለከተው የዳውንት ወረዳ ፍ/ቤት በተጠሪ መነሳት አለመነሳቱን፤ ተነስቷል ከተባለም በሰበር ደረጃ ታይቶ መወሰኑ ከአመልካች ይግባኝ መብት አንፃር ያለው አንደምታ፤ በስር የዳውንት ወረዳ ፍ/ቤት ኑዛዜ ከውርስ ነቅሎኛል የሚለው ክርክር ከተነሳ በሰበር ደረጃ የመመርመሩን ስነ-ስርዓታዊነት፤የይርጋ ክርክሩ በወረዳ ፍ/ቤት የታለፈበት አግባብ ከውርስ ህጉ፤ከፍብሄር ስነ-ስርዓት ህጉ እና የሰበር ሰሚ ችሎቱ በሰበር መዝገብ ቁጥር 37762  ከሰጠው አስገዳጅ የሰበር ውሳኔ አንፃር ተጠሪ ባሉበት ጉዳዩን አጣርቶ ለመመርመር ሲሆን ከዚሁ አንጻር ጉዳዩን እንደመረመርነዉ ተጠሪ ኑዛዜዉ እኔን ከዉርስ ይነቅለኛል የሚል ክርክር በስር ዳዉንት ወረዳ ፍርድ ቤት አንስቼ ተከራክሬአለሁ ይበሉ እንጅ አንስተዉ መከራከራቸዉን የዉሳኔዉ ግልባጭ አሳይም ፡፡የዳዉንት ወረዳ ፍርድ ቤትም በዚህ ጉዳይ ላይ ያለዉ ነገር የለም፡፡ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ሟች እናታቸዉ አደሌ ገላዉ በ2002 ዓ/ም ለግራ ቀኙ ወገኖች የደረጉትን ኑዛዜ መስረት አድርገዉ ሲሆን 2004 ዓ/ም ለሰበር አመልካቾች በሟች የተደረገዉን ኑዛዜ ያወቁት ክሱን ካቀረቡ በኋላ የሰበር አመልካቾች በሰጡት መልስ ላይ ነዉ ፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ከሟች ጤነኛ መሆን አለመሆን በተመለከተ ተጣርቶ እንዲወሰን የሚል ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን ለወረዳ ፍርድ ቤት ሲመልስ ተጠሪ በኑዛዜዉ መነቀል አለመነቀላቸዉ የህግ ጉዳይ ስለሆነ መመርመር እችላለሁ ከማለቱ በስተቀር አስቀድሞ በሰጠዉ ዉሳኔ ይህ ነጥብ በተጠሪ ክርክር ሆኖ ቀርቦ የወረዳዉ ፍርድ ቤት ዉሳኔ አልሰጠም የሚል ድምዳሜ ላይ አልደረሰም፡፡ከዉርስ ያለህጋዊ መክንያት ተነቅያለሁ የሚል የክስ ምክንያት ተጠሪ በወረዳዉ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ላይ ባለመግለጻቸዉ አመልካች የበኩላቸዉን ክርክር በዚህ ነጥብ ላይ ማሰማት እንዳልቻሉ እና ፍርድ ቤትም በዚህ ነጥብ ላይ በግልጽ የሰጠዉ ዉሳኔ እንደሌለ ተገንዝበናል ፡፡ በመሰረቱ ከዉርስ የመነቀል አለመነቀል ጉዳይ ራሱን የቻለ ክርክር የሚደረግበት ነጥብ ነዉ፡፡

በመሰረቱ በመጀመሪያ ደረጃ ጉዳዩን የተመለከተዉ ፍርድ ቤት በሰጠዉ ዉሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ለበላይ ፍርድ ቤት ይግባኙን የሚያቀርበዉ የበታች ፍርድ ቤትን ዉሳኔ ለማስለወጥ ፣ለማሻሻል ወይም ሙሉ ዉድቅ ለማድረግ ነዉ፡፡ ይህም ሊሆን የሚችለዉ ያቀረበዉ ክስ ወይም የመከላከያ ክርክር ኖሮት ያላግባብ ዉድቅ ከሆነበት ወይም የተጠየቀዉ ዳኝነት በአግባቡ ሳይታይ የታለፈ ከሆነ ነዉ ፡፡ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በይግባኝ የቀረበለትን ጉዳይ የሚያስተናግደዉ በበታች ፍርድ ቤት የተደረገዉን ክርክር እና የተጠየቀዉን ዳኝነት ይዘት እንዲሁም አግባብነቱን በመመልከት ነዉ፡፡ ስለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሚደነግገዉ የፍ/በ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) ሲታይ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ ማናቸዉም በይግባኝ የቀረበለትን ፍርድ ወይም ዉሳኔ ለማጽናት ፣ለማሻሻል ወይም ለመሻር የሚችል መሆኑን ከመደንገጉ ዉጭ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያልተጠየቀን ጉዳይ ዳኝነት የመስጠት ስልጣን ያለዉ ስለመሆኑ አያሳይም፡፡ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 182(2) የተመለከተዉ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ስልጣንም የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አስተያየት መስጠት ወይም መወሰን ይገባዉ ነበር ብሎ በሚገምተዉ ጉዳይ ላይ ትእዛዝ ወይም ዉሳኔ ለመስጠት የሚችል ስለመሆኑ በተጨማሪም ተገቢ መስሎ የታየዉን እና ነገሩን ለማስፈጸም ተስማሚ ነዉ ብሎ የሚገምተዉን ማናቸዉንም ሌላ ዉሳኔ ለመስጠት የሚችል ስለመሆኑ የተገለጸ ቢሆንም በዚህ ድንጋጌ መሰረት የተሰጡት የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ስልጣን እና ተግባራት የሚከናወኑት በበታች ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ሥርዓቱን የጠበቀ ክርክር ሲያቀርቡና የተጠየቀ ዳኝነት ሲኖር ነዉ (በሰ/መ/ቁ 37762 የተሰጠዉን የህግ ትርጉም ይመለከቷል) ፡፡ ይህ ካልሆነ አንድ ተከራካሪ በስነ ስርዓቱ መሰረት ክስ አቅርቦ ባልተከራከረበት ጉዳይ ባለመብት የሚሆንበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ በአሁኑ ጉዳይ ተጠሪ በስር ዳዉንት ወረዳ ፍርድ ቤት በሰበር አመልካቾች ላይ ያቀረቡት ክስ እናታችን ሚች አደሌ ገላዉ በህይወት ሳለች በ2002 ዓ/ም በዳዉንት ወረዳ ፍትህ ጽ/ቤት ቀርባ የመሬት ይዞታዋን ተናዛልን ወራሽነታችንንም አስወስነን ያለነዉን የዉርስ ይዞታ የሰበር አመልካቾች ይዘዉ ስለሚገኙ ድርሻችንን እንዲያካፍሉን ይወሰንልን የሚል እንጅ በ2004 ዓ/ም በተደረገ ኑዛዜ ያለህጋዊ ምክንያት ተነቅያለሁ እና ኑዛዜዉ ይፍረስልኝ በማለት ዳኝነት አልጠየቁም፡፡ ከክርክራቸዉ አቀራረብ እንደተረዳነዉ ተጠሪ ክሱን ሲያቀርቡ በ2004 ዓ/ም የተደረገ ኑዛዜ መኖሩን ቢያዉቁ ኖሮ በ2004 ሚች እናታቸዉ አደርገዉታል በተባለዉ ኑዛዜ ላይ ያህጋዊ ምክንያት ተነቅያለሁ የሚል የክስ ምክንያት መሰረት በማድረግ ክስ ማቅረብ ይችሉ ነበር ፡፡ ሆኖም ኑዛዜዉ መኖሩን ያወቁት ክስ ካቀረቡ በኋላ በቀረበዉ መልስ ላይ በመሆኑ ስለ 2004 ዓ/ም ኑዛዜ የክስ ምክንያት ለማድረግ እድሉ ነበራቸዉ ለማለት የሚቻል አይደለም ፡፡ እንዲህ በሆነ ግዜ ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት ይቻል ዘንድ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 91(1) መሰረት ክሱ እንዲሻሻል አድርጎ ግራ ቀኙ በዚያዉ አግባብ ተገቢ ነዉ የሚሉትን ክርክር ካቀረቡ በኋላ የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ሰምቶ እና መርምሮ መወሰን ይገባል፡፡ የወረዳዉ ፍርድ ቤት የ2004 ዓም ኑዛዜን የሚመለከት ክስ በግልጽ ባልቀረበበት እና በግራ ቀኙ ይህንን ኑዛዜ አስመልክቶ የተሟላ ክርክር ባልቀረበበት ለተጨማሪ አላስፈላጊ ክርክር በማይዳርግ መልኩ ህግን መሰረት ያደረገ ዉሳኔ ለመስጠት በማያስችል አግባብ ክርክሩን መምራቱን ተገንዝበናል፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ

ችሎት ደግሞ በስር ፍርድ ቤት ዳኝነት ተጠይቆበት ክርክር ያልተደረገበትን ከዉርስ የመነቀል እና ያለመነቀል ጉዳይ በሰበር ደረጃ አንስቶ የህግ ጉዳይ ነዉ በሚል ዉሳኔ መስጠቱ ከላይ የተመለከተዉን የክርክር አመራር ስርዓት የጣሰ በመሆኑ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 2013 አንቀጽ 2(4/ሀ፤ለ እና ሽ) እና 10(1/ሐ እና መ) መሰረት መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ዉሳኔ ነዉ ብለናል፡፡

በመሆኑም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ዉሳኔ**

1. የዳዉንት ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 0108822 ጥር 09 ቀን 2015 ዓ/ም ፤የሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 38751 የካቲት 01 ቀን 2015 ዓ/ም እንዲሁም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 0338316 ሀምሌ 11 ቀን 2015 ዓም በዋለዉ ችሎት የሰጡት ፍርድ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ተብሎ በሰበር ስነ ስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1) መሰረት ተሽሯል ፡፡
2. የዳዉንት ወረዳ ፍርድ ቤት የዘጋዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ የሰበር ተጠሪ ክሳቸዉን እንዲያሻሽሉ ካደረገ በኋላ በ2004 ዓ/ም በሟች እናታቸዉ ተደርጓል በተባለዉ ኑዛዜ ላይ ግራ ቀኙ የሚያቀርቡትን ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ ተገቢ ነዉ የሚለዉን ህጋዊ ዉሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩን በሰበር ስነ ስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(2) መሰረት መልሰናል ፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

**<u>ትዕዛዝ</u>**

ይህ መዝገብ ከመዝገብ ቁጥር 252811 ጋር ተጣምሮ የተመረመረ ስለሆነ ይህ ዉሳኔ የዚያም መዝገብ አካል ይሁን ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

የሰበር መዝገብ ቁጥር - 254490

ቀን 25/4/2017

ዳኞች ሺመክት አሰፋ

እንዳሻው አዳነ

አለማየሁ ሹናራ

ዋዚሙ ዋሴራ

ዘውዲቱ ታደሰ

አመልካች - ቻይና ሬል ወይስ ሰቨንዝ ግሩፕ ኦሞ ወንዝ ታርጫ መንገድ ስራ ድርጅት - አልቀረቡም

ተጠሪ - አቶ ደረሰ ደሳለኝ - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች በቀን 23/02/2016 አ.ም ፅፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የዳውሮ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 16786 በቀን 24/08/2015 አ.ም የሰጠውን ውሳኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ታርጫ ምድብ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 18418 በቀን 12/12/2015 አ.ም በትዕዛዝ ማፅናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊሻር ይገባል  በማለት አቤቱታቸውን በማቅረባቸው ነው፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው በሥር ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች ተከሳሽ የአሁን ተጠሪ ከሳሽ የነበሩ ሲሆን የአሁን ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ይዘት በሎማ ባሳ ወረዳ ቱልማ ማማ ቀበሌ አራዳ ንዕስ በግምት 0.732 ሄክታር በሆነው ይዞታቸው ላይ ያለሙትን ባህር ዛፎች የአሁን አመልካች ከይዞታቸው ጋር በስተደቡብ በሚዋሰነው ይዞታ ላይ ይዞታ በመከራየት ቆሻሻ አፈርና ጉቶዎች ሲያከማቹ ግማሹን የተንሸራተተው አፈር ይዞት ሲሄድ ቀሪው ግማሽ ደግሞ የደረቀ በመሆኑ ለደረሰው ጉዳት የአሁን አመልካች ብር 800,800 (ስምንት መቶ ሺህ ስምንት መቶ ) እና ለዳኝነት፣ ለጠበቃና ልዩ ልዩ ወጪዎች እንዲከፍሉኝ በማለት ክሳቸውን አቅርበዋል፡፡ የአሁን አመልካች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና አማራጭ መልስ ያቀረቡ ሲሆን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያቸው ውድቅ ተደርጓል፡፡ የአማራጭ መልሳቸው ይዘት የተከመረው አፈር አልተንሸራተተም፣ በይዞታውና በባህር ዛፎቹ ላይ ምንም ጉዳት አላደረሰም እንጂ ደርሷል ቢባል እንኳን ኃላፊነቱ መሬቱን ያከራዩት እንጂ የመሬቱ ተከራይ አይደለም፡፡ ንብረቱን የገመቱት አካላት ለመገመት የሚያስችል የውልም ሆነ የህግ ስልጣን የሌላቸው በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡

የዳውሮ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ክስ በሚሰማበት ጊዜ የአሁን አመልካች ባለመቅረባቸው በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ አንቀፅ 70(ሀ) መሰረት ጉዳዩ በሌሉበት የተሰማ ሲሆን የአሁን ተጠሪ ቀርበው ምስክሮቻቸውን በማቅረብ አሰምተዋል፡፡ የቀረቡት ሶስት ምስክሮች በአሁን ተጠሪ ባህር ዛፎች ላይ ጉዳት መድረሱን የጉዳቱም መጠን 900,000 ብር (ዘጠኝ መቶ ሺህ ብር) መሆኑን ያስረዱ ሲሆን የጉዳት መጠኑን በተመለከተ የዳውሮ ዞን እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት መምሪያ ባለሞያ 932,315 ብር (ዘጠኝ መቶ ሰላሳ ሁለት ሺህ ሶስት መቶ አስራ አምስት ብር) ጉዳት ደርሷል በማለት ሪፖርት አቅርቧል፡፡ የአሁን ተጠሪ ቀደም ብለው ያስገመቱት የወቅቱን ገበያ ያላገናዘበና ዝቅ ያለ ሲሆን ከዞኑ ግብርና መምሪያ የቀረበው ግምት የወቅቱን የገበያ ዋጋ ያገናዘበ ነው ተብሎ ይገመታል በመሆኑም የአሁን አመልካች ለአሁን ተጠሪ የጉዳት 932,315 ብር (ዘጠኝ መቶ ሰላሳ ሁለት ሺህ ሶስት መቶ አስራ አምስት ብር)፣ ለዳኝነት የተከፈለ 10,930 ብር (አስር ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰላሳ ብር)፣ ወጪና ኪሳራ በርትዕ 10,000 ብር (አስር ሺህ ብር)፣ የጠበቃ አበል 10% 93,231.50 ብር (ዘጠና ሶስት ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ አንድ ብር ከሃምሳ ሳንቲም)፣ በድምሩ 1,046,476.50 ብር (አንድ ሚሊዮን አርባ ስድስት ሺህ አራት መቶ ሰባ ስድስት ብር ከሃምሳ ሳንቲም) ሊከፍሉ ይገባል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት የአሁን አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 18418 ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም በቀን 05/12/2015 አ.ም ይግባኙ አያስቀርብም በማለት ሰርዞታል፡፡ የአሁን አመልካች በነዚህ ውሳኔዎች ላይ ቅር በመሰኘት ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በቀን 23/02/2016 አ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ተጠሪ በክሳቸው እንዲወሰንላቸው የጠየቁት የዳኝነት መጠን ብር 800,800 (ስምንት መቶ ሺህ ስምንት መቶ ብር) ካሣ ሆኖ እያለ ህጉን ባልተከተለ መንገድ፣ ገለልተኛ ባልሆኑ ሰዎችና ቦታው ላይ እንዳልገኝ ተደርጎ ከቅን ልቦና ውጪ  ከሳሽ ከጠየቀው ዳኝነት በላይ የተሰራዉ የባለሞያ ማጣሪያ አመልካችን እጅግ የሚጎዳ በመሆኑና የሞያው ባለቤት በሆነው በከርሰ ምድር ባለሞያ እንዲጣራ ተደርጎ የተጎዳ ንብረት ካለ በግራ ቀኙ ገማች ኮሚቴ አባላት ተመርጠው እንዲገምቱ ተደርጎ ውሳኔ እንዲሰጠኝ በስር ፍርድ ቤት ጠይቄ እያለ ይህ ሳይደረግ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ተሽሮ ከወጪና ኪሳራ ጋር እንዲወሰንልኝ በማለት የሰበር አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበውን የሰበር አቤቱታ ከስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔና ከተገቢው ህግ ጋር አጣምሮ በመመርመር በሥር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ከተጠየቀው ዳኝነት በላይ መሆን አለመሆኑን ከፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 182 እና በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁጥር 33945፣ 86551 ከተሰጡ የሕግ ትርጉሞች አንጻር አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ጉዳዩ በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 እንቀጽ 28(3) ያስቀርባል ተብሏል ተጠሪም በቀረበው ቅሬታ ላይ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተገቢ ነው የሚሉበትን ምክንያት በመዘርዘር ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የግራቀኙን ክርክር፣ የሥር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ እንዲሁም የተያዘውን ጭብጥ እና ሕጉን መነሻ በማድረግ ውሳኔው ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ተጠሪ ከጅምሩ ክስ ሲያቀርቡ ጉዳት ደረሰብኝ በማለት ገምተው ያቀረቡት የገንዘብ መጠን ብር 800800 (ስምንት መቶ ሺ ስምንት መቶ ነው)፡፡ ከዚህ በኋላ በክርክር ወቅት ፍርድ ቤት ሲያስገምት በክሱ ላይ ከሳሽ ከገለጹት ገንዘብ በላይ ተገመተ በማለት ነው ከቀረበው ክስ በላይ ሊወሰን የቻለው፡፡የሆነው ሆኖ ከሳሽ በግልጽ ዳኝነት ባልጠየቁበት ወይም ከጠየቁት ገንዘብ በላይ የተሰጠው ውሳኔ የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 182(2) ን የሚቃረን እና ከባለቤቱ በላይ ማወቅ የሚመስል ነው፡፡ በርግጥ በዚህ ችሎት ከሳሽ(ተጠሪ) ባቀረቡት ክርክር ግምት በኋላ ስለጨመረ ይጽናልኝ ብለዋል፡፡ የሆነው ሆኖ ዳኝነት ያልጠየቁበትን ገንዘብ መጠን እንዲወሰንላቸው ለማድረግ የሚደግፋቸው ህግ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

የለም፡፡ የስር ፍርድ ቤቶችም ቢሆኑ የገንዘቡን መጠን በተጠየቀው ዳኝነት ልክ መቀነስ ነበረባቸው፡፡ በመሆኑም የዳኝነት የጠበቃ አበልና ሊሎች ወጪ ኪሳራን ጨምሮ አጠቃላይ ከተወሰነው ብር 1046476.50 (አንድ ሚሊየን አርባስድስት ሺአራት መቶ ሰባስድስት ከሀምሳ ሳንቲም) ከተጠየቀው ዳኝነት በላይ የተገመተው ብር 131515(አንድ መቶ ሰላሳ አንድ ሺ አምስት መቶ አስራ አምስት) ሲቀነስ ሊከፈል የሚገባው አጠቃላይ ገንዘብ ብር 914961.50(ዘጠኝ መቶ አስራ አራት ሺ ዘጠኝ መቶ ስልሳ አንድ ከሀምሳ ሳንቲም) በመሆኑ የህጉ ስተት ሊታረም ይገባል ብለን ከዚህ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

- ዳውሮ ዞን ከ/ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር16786 በ24/7/2015 እንዲሁም የደ/ም/ኢ/ህ/ክ/መ/ጠ/ፍርድቤት በመ/ቁ18418 በ12/12/2015 የሰጡትን ውሳኔ በሰበር/ስ/ስ/መመርያ/ቁ 17/2015 አንቀጽ 9(1)(ለ) መሰረት አሻሽለን አመልካች በአጠቃላይ ለተጠሪ ብር 914961.50(ዘጠኝ መቶ አስራ አራት ሺ ዘጠኝ መቶ ስልሳአንድ ከአምሳሳንቲም) ሊከፍል ይገባል ብለን ወስነናል፡፡
- በዚህ መዝገብ በጥቅምት 27/2016 የተሰጠው እግድ ተነስቷል፡፡
- የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ ይቻቻሉ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

*የሰ/መ/ቁ 255911*

ታህሳስ 24 ቀን 2017ዓ.ም

ዳኞች ፡- ገበየሁ ፈለቀ

ደረጀ አያና

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

ብርሃኑ መንግሥቱ

አመልካች፡- አቶ ሰንበቶ ዶጊሶ ቀርቧል

ተጠሪ ፡- ወ/ሮ ብዙነሽ የኋላሸት አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ጉዳዩ የጋብቻ ፍቺ በንብረት ረገድ የሚያስከትለዉን ዉጤት ለመወሰን የዳኝነት ሥልጣን የሚኖረዉን ፍርድ ቤት የሚመለከት ነዉ፡፡ክርክሩ የተጀመረው በሲዳማ ክልል በሀዋሳ ከተማ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች በተጠሪ ላይ በመሠረቱት ክስ - በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ በዚሁ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 3197 ላይ በቀን 03/02/2015 ዓ.ም በተሰጠው ዉሳኔ ፈርሷል፡፡ በጋብቻ በቆየንበት ወቅት ያፈራነዉ የጋራ ሀብት የሆነ በአዲስ አበባ ከተማ ዉስጥ በይዞታ መለያ ቁጥር 000060602004 የተመዘገበ ስፋቱ 203 ካሬ ሜትር ላይ ያረፈ የመኖሪያ ቤት እና 3 ክፍል ሰርቪስ ቤት አለን፡፡ እንዲሁም የቤት ዕቃዎች ቁምሳጥን ከነዕቃው፣ፍሪጅ፣የኮካ ሳጥን በቁጥር 2፣የሚሪንዳ ሳጥን በቁጥር 2 የጊዮርጊስ ቢራ ሳጥን አለን፡፡ በመሆኑም ተጠሪ እነዚህን ንብረቶች እንዲያካፍሉኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

**<u>ማስታወሻ</u>፡** - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

ተጠሪም በመልሳቸው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን ያቀረቡ ሲሆን ዝርዝሩም፡-የተጠሪ ዋና አድራሻ አዲስ አበባ ከተማ በመሆኑ በፌዴራል ፍርድ ቤት አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 5/5 መሠረት ጉዳዩ የፌደራል ፍርድ ቤት ስልጣን ስለሆነ ፍርድ ቤቱ ይህንን ጉዳይ ለመዳኘት ሥልጣን የለውም፡፡እንዲሁም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 19 መሠረት ጉዳዩን ለመመልከት አካባቢያዊ ስልጣን የለውም፡፡ይህ ጉዳይ ከዚህ በፊት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መ/ቁጥር 22518 ላይ በቀን 08/11/2006 ዓ.ም ዉሳኔ በመስጠት ያለፈ ጉዳይ ስለሆነና እንዲሁም በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች እና ተጠሪ በመስማማት የታረቁበትን ዉል በቀን 24/07/2006 ዓ.ም ፍርድ ቤት በማጠናከር ጉዳዩ በዉሳኔ እና በእርቅ የተጠናቀቀ ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5/1 መሠረት ክስ ማቅረብ አይቻልም፡፡አመልካች በፍ/ብሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 33/2 እና 33/3 መሠረት ክስ የማቅረብ መብት የላቸዉም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ በሰጠዉ ዉሳኔ በተለያዩ ክልል የሚኖሩ ሰዎች ጉዳይ የፌዴራል ፍርድ ቤት ጉዳይ ቢሆንም የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዉክልና እንደሚያይ በሕገ-መንግስቱ እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 5/11 ስር የተገለፀ በመሆኑ ይህ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ሥልጣን አለው፡፡አንድ ክስ መቅረብ ያለበት ተከሳሹ በሚኖርበት አድራሻ ሲሆን ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ንብረትም በአዲስ አበባ ከተማ ዉስጥ ያለ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁጥር 19/1 መሠረት ይህ ፍርድ ቤት አካባቢያዊ ስልጣን ስለሌለዉ ጉዳዩን ለመዳኘት ሥልጣን የለውም በማለት ተጠሪ በዚህ ረገድ ያቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በመቀበል ወስኗል፡፡ እንዲሁም ክስ የቀረበበት ጉዳይ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነዉ አመልካች ክስ ለማቅረብ መብት የላቸዉም በማለት ተጠሪ ያቀረቧቸዉን መቃወሚያዎች በመቀበል ክሱን ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለሲዳማ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 05408 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 22/10/2015ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ የሥር ፍርድ ቤት አካባቢያዊ ሥልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ብይን በውጤት ደረጃ ትክክል ነው በማለት በዚህ ረገድ የተሰጠዉን ዉሳኔ በማጽናት፤ ነገር ግን የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለመዳኘት ሥልጣን የለኝም ባለበት ሥልጣን ያለዉ ፍርድ ቤት መመርመር ያለበትን ሌሎች መቃወሚያዎችን በመመርመር የሰጠዉ ዉሳኔ ክፍል ያለሥልጣኑ የሰጠዉ ዉሳኔ በመሆኑ ስህተት ነዉ በማለት በመሻር ወስኗል፡፡በመቀጠል አመልካች በዚህም ውሳኔ ቅር በመሰኘት አቤቱታቸዉን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ቢሆንም ችሎቱ በመ/ቁጥር 01699 ላይ በቀን 10/12/2015ዓ.ም በሰጠዉ ትእዛዝ ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ ስህተት የለበትም በማለት አቤቱታቸውን ሠርዞባቸዋል፡፡

አመልካች በቀን 01/04/2016ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታቸውን ያቀረቡት ከላይ በተገለፀው መሰረት በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ሲሆን ይዘቱም በአጭሩ፡-የጋብቻ ፍቺ ውሳኔ የሰጠው የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሆኖ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 19 ጠቅሶ አቤቱታዬን ዉድቅ ማድረጉ

መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው፡፡የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 19 ለሕገ መንግሥቱ ተገዥ እንጂ ሕገ መንግሥቱን እንዲቃረን ተደርጎ ትርጉም ሊሰጠዉ አይገባም፡፡ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሕገ መንግሥት የተሰጠዉን አከራክሮ የመወሰን ሥልጣን ወደ ጎን በመተዉ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 5/ሸ ድንጋጌን ባለመከተል የተሰጠዉ ትእዛዝ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ሳያርም በማለፉ የሰጠዉ ዉሳኔ በሰ/መ/ቁጥር 139912 (ቅፅ 12) የሕግ ትርጉም የሚቃረን ነዉ ተብሎ ተሽሮ ይወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

ይህ ችሎትም የሀዋሳ ከተማ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በግራ ቀኙ መካከል የነበረውን ጋብቻ በፍቺ ውሳኔ ቀሪ ካደረገ በኂላ ይህንኑ ተከትሎ በአሁኑ አመልካች የቀረበለትን የጋራ ንብረት ክፍፍል አቤቱታ ለማየት የዳኝነት አካባቢያዊ ስልጣን የለኝም በሚል ውድቅ ያደረገበት እና ይኸው ዉሳኔ እስከ ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ተቀባይነት ያገኘበት አግባብ፤ እንዲሁም ጉዳዩ የባል እና ሚስት ክርክር ሆኖ እያለ ክርክሩ ከከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊጀምር የቻለበት አግባብ ይኸው ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 119582 እና 127714 ላይ ከሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም አንፃር እንዲመረመር ተጠሪ መልስ እንዲሰጡ አዝዟል፡፡

ተጠሪ በቀን 29/01/2017 ዓ.ም ባቀረቡት መልስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 19 መሰረት ማንኛውም ክስ መቅረብ የሚገባው ተከሳሹ በሚኖርበት ወይም ለግል ጥቅሙ በሚሰራበት ክፍል በሚያስችለው ባለስልጣን ፍርድ ቤት ነዉ፡፡በመሆኑም ተጠሪ የምኖረውም ሆነ ንብረቱ የሚገኘዉ በአዲስ አበባ ከተማ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት አካባቢያዊ ስልጣን የለኝም ማለቱ አግባብ ነው፡፡የሥር ፍርድ ቤት የፍቺ ውሳኔ ከመስጠት በዘለለ ንብረት ይካፈሉ ሲል የሰጠው ውሳኔ የለም፡፡በፍቺ ክርክሩ ላይም ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ተቀብሎ ለማየት የሥረ ነገርም ሆነ የአካባያዊ የዳኝነት ስልጣን የለውም የሚልና ሌሎችም መቃወሚያዎችን ያቀረብኩ ቢሆንም የሥር ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 127714 ላይ የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በማለፍ የፍቺ መዝገቡን አይቶ ውሳኔ የሰጠ ቢሆንም በአቅም እጥረት ይግባኝ አልጠየቅኩም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤት ሥልጣን የለኝም በማለት መዝገቡን በብይን መዝጋቱ አግባብ ነው ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

ከላይ አጠር ባለ መልኩ የተገለፀው የግራ ቀኙ ክርክር እና የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ይዘት የሚመለከት ሲሆን እኛም ከፍ ሲል የተጠቀሱትን ጭብጦች መሠረት በማድረግ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል መሰረታዊ የሕግ ስህተት መፈጸም አለመፈጸሙን እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የነበረዉ ጋብቻ በሲዳማ ብሔራዊ ክልል በሀዋሳ ከተማ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 3197 ላይ በቀን 03/02/2015 ዓ.ም በተሰጠ ዉሳኔ በፍቺ እንደፈረሰ በግራ ቀኙ የታመነ ጉዳይ ነዉ፡፡የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የጋብቻ ፍቺ የተጠየቀበትን ክስ ተቀብሎ

የዳኝው አመልካች የክልሉ ነዋሪ ተጠሪ ደግሞ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነዋሪ በመሆናቸዉ መነሻ እንደሆነ ተገንዝበናል ።

በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 5(1/ሀ) እና አንቀጽ 12(2/ሀ) መሰረት የቤተሰብ ጉዳይ በጠቅላላዉ በተለይ ደግሞ የጋብቻ ፍቺ ጉዳይ የሕግ ምርጫ (choice of law) እና የብሔራዊ ዳኝነት ሥልጣን (judicial jurisdiction) ጥያቄዎችን በማስነሳት በግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግ (private international law) ማዕቀፍ ዉስጥ እንዲታይ የሚያደርግ ሁኔታ ሲኖር በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን ሊታይ ይችላል፡፡በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 50(5 እና 7)፣52(1 እና 2) ፣51 እንዲሁም 55 ጣምራ ንባብ መሰረት የቤተሰብ ሕግ የማዉጣትና በሕጉ የሚሸፈኑ ጉዳዮች የመዳኘት ሥልጣን እንደቅደምተከተላቸዉ የክልል ምክር ቤት እና የክልል ፍርድ ቤቶች ነዉ፡፡ በተያዘዉ ጉዳይ እንዲፈርስ የተጠየቀዉ ጋብቻ በግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግ (private international law) ማዕቀፍ ዉስጥ እንዲታይ የሚያደርግ ሁኔታ አለበት የሚል አሊያም ከጋብቻ ምስረታ፣አፈጻጸም እና በፍቺ መፍረስና ከፍቺ ዉጤት ጋር በተያያዘ በኢትዮጵያ ዉስጥ የሚገኙ የሁለት ክልሎችን ቤተሰብ ሕግ ምርጫ የሚመለከት እና ከክልሎች ክልላዊ የዳኝነት ሥልጣን ጋር የተያያዘ ክርክር አልተነሳም፡፡

እንዲሁም የጋብቻ ፍቺ ጉዳይ የተነሳዉ በአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተሞች ነዋሪዎች መካከል ከሆነ ደግሞ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 14፣በፌዴራል ቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 108 እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 18 መሰረት በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን የሚታየዉ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል በሰ/መ/ቁጥር 119582 እና 127714 ላይ በተሰጠዉ የሕግ ትርጉም ላይ እንደተመለከተዉ በአገራችን ባለውና የፌዴራል አካል በሆነው ክልል መንግስት በወጣው የቤተሰብ ሕግ መሰረት ጋብቻው ሲፈጸም የጋብቻ እና የጋብቻ ፍቺ ውጤት ክርክር መፍትሄ ሊያገኝ የሚገባው ጋብቻው በተፈጸመበት ሕግ አግባብ እንደሆነ፤ ጋብቻው የተፈጸመው በአንድ ክልል ውስጥ እና በዚያው ክልል የቤተሰብ ሕግ መሰረት በሆነ ጊዜ ከፍቺ ጋር ተያይዞ ጥያቄ በተነሳበት ወቅት ተጋቢዎቹ በተለያዩ ምክንያቶች የሚኖሩት በተለያዩ ክልሎች ውስጥ መሆኑ ቢረጋገጥ እንኳ ከፍቺ እና መሰል ጥያቄዎች ጋር ተይይዘው የሚነሱ ጉዳዮችን የማስተናገድ የስረ ነገር ስልጣን በክልሉ ሕግ መሰረት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የተሰጠው የክልሉ ፍርድ ቤት ከሚሆን በቀር ተጋቢዎቹ መደበኛ ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች ውስጥ እንደሆነ ተቆጥሮ ጉዳዩ ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5/2 [ይህ አንቀጽ በአሁኑ ጊዜ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 5(1/ሸ) መተካቱን ልብ ይሏል፡፡] ድንጋጌ አንጻር በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ሥልጣን ስር የሚወድቅ ነው ሊባል የሚችልበት የሕግ አግባብ የለም ሲል የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

የጋብቻ ፍቺ በተመለከተ ዳኝነት ተጠይቆበት የሚቀርብ ክስ በገንዘብ ግምት ሊወሰን የሚችል ክስ አይደለም፡፡ በመሆኑም በፍቺ እንዲፈርስ የተጠየቀዉ ጋብቻ ከአዲስ አበባ እና ከድሬዳዋ ጋር የሚያያዝ

ካልሆነ የጋብቻ ፍቺ እና ዉጤቱ በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን ለመዳኘት ሥልጣን የሚኖረዉ በክልል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ላይ የሚደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 18 መሰረት ጋብቻዉ በተፈጸመበት ክልል የሚገኝ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነዉ፡፡

በያዝነዉ ጉዳይ ግራ ቀኙ በክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 3197 ላይ የጋብቻ ፍቺ ክርክር ባደረጉበት ጊዜ በግራ ቀኙ መካከል የነበረዉ ጋብቻ በሲዳማ ክልል ዉስጥ እንደተፈጸመ በመግለጽ ያሰሙት ክርክር ስለመኖሩ በዚህ የክርክር ደረጃ በግልጽ የቀረበ ነገር የለም፡፡ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የጋብቻ ፍቺ ጥያቄዉን ተቀብሎ በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን አይቶ በመ/ቁጥር 3197 ላይ በቀን 03/02/2015 ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ በግራ ቀኙ መካከል ተደርጎ የነበረዉ ጋብቻ በፍቺ እንዲፈርስ ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡ፍርድ ቤቱ የጋብቻ ፍቺ ጥያቄ ተቀብሎ ሊወስን የቻለዉ አመልካች መደበኛ ነዋሪነታቸዉ በሲዳማ ክልል ሲሆን ተጠሪ ደግሞ መደበኛ ነዋሪነታቸዉ በአዲስ አበባ ከተማ ዉስጥ ነዉ በሚል በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 80/5 ፣ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 5(1/ሸ) እና አንቀጽ 14/1 እንዲሁም በሲዳማ ብሔራዊ ክልል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 4/2012 አንቀጽ 8(1/መ) ስር በተደነገገዉ መሰረት ጉዳዩ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሚዳኝ በመሆኑ በዉክልና የመዳኘት ሥልጣን አለኝ በሚል ነዉ፡፡በዚህ በተያዘዉ መዝገብ ላይ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የጋብቻ ፍቺ ጥያቄ ተቀብሎ ለመዳኘት ሥልጣን የለዉም በሚል በመ/ቁጥር 3197 ላይ በተሰጠ ዉሳኔ ላይ ሳይሆን ፍርድ ቤቱ የጋብቻ ፍቺ በንብረት ረገድ የሚያስከትለዉን ዉጤት እንዲወስን የተጠየቀዉን ለመዳኘት ሥልጣን የለኝም በማለት በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ ነዉ፡፡ በመሆኑም በሌላ መዝገብ ላይ የተሰጠ የጋብቻ ፍቺ ዉሳኔ ጸንቶ ባለበት በተጠቀሰዉ መነሻ ምክንያት የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የጋብቻ ፍቺ ጥያቄዉን እንደ ፌዴራል ጉዳይ ቆጥሮ በመዳኘት የጋብቻ ፍቺ ዉሳኔ መስጠቱ ተገቢ ነዉ ወይስ አይደለም የሚለዉ በሰ/መ/ቁጥር 119582 እና 127714 ከተሰጠዉ የሕግ ትርጉም አንጻር መመርመር ሥነ ሥርዓታዊ ስለማይሆን አልፈነዋል፡፡

ወደ ያዝነዉ ጉዳይ በመመለስ የዚህን ችሎት ዉሳኔ የሚሻዉን *የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የጋብቻ ፍቺ ከወሰነ በኋላ የቀረበለትን የንብረት ክፍፍል ጥያቄ ለመዳኘት ሥልጣን የለኝም ብሎ በመወሰኑ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡*በነባሩ ክልል የወጡ አዋጆች በሲዳማ ብሔራዊ ክልል ተፈጻሚነታቸዉ እንዲቀጥል ለመፍቀድ በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 8/2012 መሰረት የቀድሞዉ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 75/1996 ለዚህ ጉዳይ ተፈጻሚነት አለዉ፡፡ በዚህ ሕግ አንቀጽ 93፣96 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሰረት የንብረት ክፍፍል ጉዳይ ባልና ሚስቱ የጋብቻቸዉ መፍረስ በንብረት በኩል የሚያስከትለዉ ዉጤት በምን አግባብ ዉሳኔ እንደሚሰጥ ተደንግጓል፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት የንብረት ክፍፍል ጥያቄ ሊቀርብ የሚገባዉ የጋብቻ ፍቺ ዉሳኔ ተከትሎ እንደመሆኑ ፍቺ በተወሰነበት መዝገብ ላይ እንጂ ሌላ ክስ በማቅረብ በአዲስ መዝገብ ላይ ታይቶ የሚወሰን

አይደለም፡፡በመሆኑም የጋብቻ ፍቺ የወሰነዉ ፍርድ ቤት በዚያዉ መዝገብ ላይ የንብረት ክፍፍል ጥያቄ ሲቀርብለት ሕግንና ማስረጃን መሰረት በማድረግ የሚወስነዉ ጉዳይ እንደመሆኑ ክፍፍል የተጠየቀበት ንብረት የሚገኝበት ቦታ(የአስተዳደር ክልል) ከግምት ዉስጥ ሳይገባ ዉሳኔ የሚሰጥበት ይሆናል፡፡በዚህ መልኩ በክልሉ አስተዳደር ወሰን ዉስጥ በማይገኝ ንብረት ላይ ዉሳኔ ቢሰጥ የፍርድ አፈጻጸሙ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ስለፍርድ አፈጻጸም በተዘረጋዉ ሥርዓት መሰረት ጭምር ሊመራ የምችልበት በቂ የሕግ ማዕቀፍ በመኖሩ ከፍርድ አፈጻጸም አኳያ የሚፈጠር ጉልህ ችግር አይኖርም፡፡

የግዛት ክልል ዳኝነት ሥልጣን በሚመለከተዉ ምዕራፍ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 19 ስር በመርህ ደረጃ እንደተመለከተዉ ማንኛዉም ክስ መቅረብ የሚገባዉ ተከሳሹ በሚኖርበት ወይም ለግል ጥቅሙ በሚሠራበት ከፍል በሚያስችለዉ ሥልጣን ባለዉ ፍርድ ቤት ነዉ፡፡ይህ መርህ ተፈጻሚ የማይሆንበት ሁኔታ ደግሞ በዚሁ ድንጋጌ ላይ እንደተመለከተዉ ሌሎች ፍርድ ቤቶች ክሱን እንዲቀበሉ በሌላ ሕግ ላይ ሥልጣን ሲሰጥ ነዉ፡፡ከላይ እንደተመለከተዉ የቤተሰብ ሕጉ በደነገጋቸዉ ሥነ ሥርዓታዊ ባህሪይ ባላቸዉ ድንጋጌዎች መሰረት ንብረቱ የሚገኝበት ቦታ ወይም ተከሳሹ የሚኖርበት ወይም ለግል ጥቅሙ የሚሠራበት ስፍራ ከግምት ሳይገባ የጋብቻ ፍቺ በተወሰነበት መዘግብ ላይ የንብረት ክፍፍል ጥያቄ ቀርቦ ዉሳኔ እንደሚሰጥ በልዩ ሕጉ በልዩ ሁኔታ ተደንግጓል፡፡

በመሆኑም የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የጋብቻ ፍቺ ከወሰነ በኋላ የቤተሰብ ሕጉ የዘረጋዉን የንብረት ክፍፍል ጥያቄ አቀራረብና ዉሳኔ አሰጣጥ ተከትሎ ክርክሩን በመምራት የጋብቻ ፍቺ በተወሰነበት መዝገብ ላይ የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ መወሰን ነበረበት፡፡ሆኖም ለዚህ ጉዳይ ተፈጻሚነት የሌለዉን የሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌ መሰረት በማድረግ የዳኝነት ሥልጣን የለኝም በማለት ዉሳኔ መስጠቱም ሆነ በየደረጃዉ ያሉ ፍርድ ቤቶች ይህንን ዉሳኔ ማጽናታቸዉ በኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 37/1 መሰረት ጥበቃ የተደረገለትን የአመልካችን ፍትህ የማግኘት መብት ያጣበበ፣በሰ/መ/ቁጥር 119582 ላይ የተሰጠዉን የሕግ ትርጉም እና የክልሉን የቤተሰብ ሕግ የሚቃረን በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሀ እና ሸ) እና 10(1/ሐ) መሰረት ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## <u>ዉሳኔ</u>

1. የሀዋሳ ከተማ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 1524/15 ላይ በቀን 21/06//2015 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የሲዳማ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 05408 ላይ በቀን 22/10/2015ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 01699 ላይ በቀን 10/12/2015ዓ.ም የሠጠዉ ትእዛዝ በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 መሠረት ጸንተዋል፡፡

2. በግራ ቀኙ መካከል የነበረዉን ጋብቻ በፍቺ እንዲፈርስ ዉሳኔ የሰጠዉ የሀዋሳ ከተማ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዚያዉ መዝገብ ላይ ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ሌሎች ክርክሮች ጭምር መርምሮ የጋብቻ መፍረስ በንብረት ረገድ የሚያስከትለዉን ዉጤት የመወሰን የዳኝነት ሥልጣን አለዉ ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. አመልካች የጋብቻ መፍረስ በንብረት ረገድ በሚያስከትለዉ ዉጤት ላይ ዉሳኔ እንዲሰጥ በመ/ቁጥር 3197 ላይ አቤቱታ በማቅረብ የመጠየቅ መብት አላቸዉ ብለናል፡፡
4. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት በነበረዉ ክርክር ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

## <u>ትእዛዝ</u>

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ግራ ቀኙ ሲጠይቁ ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. ዉሳኔዉ በቀን 09/05/2017 ተነብቦ መዝገቡ ተዝግቷል ፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

የሰ/መ/ቁ 256185

ታህሳስ 24 ቀን 2017ዓ/ም

ዳኞች ፡- ገበየሁ ፈለቀ

ደረጀ አያና

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

ብርሃኑ መንግሥቱ

አመልካች፡-የቻይና ኮሚኒኬሽን ኮንስትራክሽን ካምፓኒ - ጠበቃ መድሃኔ ታደለ - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡-1. ወ/ሮ ለምለም ተሾመ - ቀረቡ

2. ኤስ ደብልዩ ኤስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር

3. የኢትዮጲያ ምድር ባቡር ኮርፖሬሽን - የቀረበ የለም

4. የራያ ቆቦ ወረዳ አስተዳደር

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የጉዳት ካሳን የሚመለከት ነው፡፡ክርክሩ በተጀመረው የሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን 1ኛ ተጠሪ ከሳሽ፣2ኛ ተጠሪ ተከሳሽ እንደዚሁም አመልካች፣3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ጣ/ገብ በመሆን ተከራክረዋል፡፡1ኛ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት የክስ ይዘት በአጭሩ 2ኛ ተጠሪ በራያ ቆቦ ወረዳ 01

ቀበሌ የሚገኘውን ይዞታዬን የባቡር መንገድ ድልድይ ሲሰራ መሬቴን ሙሉ በሙሉ በጎርፍ በማስወሰድ ዘላቂ ጉዳት ያደረሰብኝ በመሆኑ የ1ዓመት አላባ 28,800 ሲሆን የ10 ዓመት አላባ 288,000 (ሁለት መቶ ሰማኒያ ስምንት ሺህ) እንዲሁም መሬት ሙሉ በሙሉ የተጎዳ በመሆኑ ምትክ መሬት እንዲሰጠኝ አልያም ብር 200,000 (ሁለት መቶ ሺህ) ካሳ እንዲከፈለኝ የሚል ነው፡፡2ኛ ተጠሪም በሰጡት መልስ በንዑስ ተቋራጭነት የዋናው ስራ ተቋራጭ ከሆነው አመልካች በተሰጠን ዲዛይን መሠረት የሠራን ሲሆን ከተሰጠን ዲዛይን ውጭ የሠራነው ነገር የሌለ በመሆኑ አመልካች ወደ ክርክሩ እንዲገባልን ሚል ነው፡፡አመልካችም ወደ ክርክሩ እንዲገባ ተደርጎ ክሱ በይርጋ የሚቋረጥ ነው በሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን በፍሬ ነገር ላይም በሰጡት መልስ የሠራነውን የባቡር ድልድይ ዲዛይን 3ኛ ተጠሪ ምንም አይነት ችግር የሌለበት መሆኑን አረጋግጦ ያፀደቀው ነው፣ጉድለት ካለበትም ሰሪው ተከሳሽ ስለሆነ ኃላፊነት ያለባቸው ተከሳሽ እና 3ኛ ተጠሪ ናቸው፣ጉዳቱ የደረሰው ተፈጥሮአዊ በሆነ ጎርፍ ምክንያት ነው እንጂ ድልድዩ በመሰራቱ ምክንያት አይደለም፡፡መሬቱ ካሳ የተከፈለበት ነው በሚል 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ወደ ክርክሩ እንዲገቡ ትዕዛዝ እንዲሰጥ የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡3ኛ ተጠሪም ይርጋን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት በማንሳት የተከራከሩ ሲሆን በፍሬ ነገር ክርክራቸውም መሬቱ ካሳ የተከፈለበት ነው፣ ከተከሳሽ ጋር ምንም አይነት ውል የለንም፣ውላችን ከአመልካች ጋር ሲሆን በውላችን አግባብ ማንኛውንም ኃላፊነት የሚወስደው ራሱ ተቋራጩ ነው ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ፍ/ቤቱም በዲዛይኑ ውስጥ የፍሳሽ ማስወገጃው ከድልድዩ የሚወጣውን ጎርፍ ተከትሎ ቋሚ ስራ ያልተሰራለት ስለመሆኑ በቀረቡት ምስክሮች ተረጋግጧል፣የፍሳሽ ማስወገጃ በዲዛይን ውስጥ ስራውም ተካቶ አልተሰራም፣የባቡር መስመር ስራውን ዲዛይን የሚሰራው አመልካች ሲሆን የሚያፀድቀው ደግሞ 3ኛ ተጠሪ በመሆኑ ያልተነጣጠለ ኃላፊነት አለባቸው፣ለከሳሽ የሚከፈለውን የጉዳት ካሳ በተመለከተ የ2008 እና የ2009 አላባ በ2 ዓመት ይርጋ የተቋረጠ ሲሆን የ2010 ለ2011 እና የ2011 ለ2012 ያለው የሰሜን ወሎ ዞን ገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም በላከው ውጤት አግባብ እና የቀሪው የ10 ዓመት ዘላቂ የመፈናቀል ካሳ የአመቱ በ10 ዓመት ተባዝቶ በመጣው ውጤት ሊወሰን ይገባል በማለት በአጠቃላይ 375,060 ባልተነጣጠለ ኃላፊነት እንዲከፍሉ በሚል ወስኗል፡፡

አመልካች እና 3ኛ ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም የሁለቱንም የይግባኝ አቤቱታ በማጣመር በሰጠው ውሳኔ ጉዳቱ የደረሰው የውሀ ማፍሰሻ ቦይ ዲዛይን ባለመሰራቱ ሲሆን የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዲዛይኑን የመስራት በውል የተቀመጠ ኃላፊነት ያለበትን አመልካችን ብቻ ለጉዳቱ ሃላፊ ማድረግ ሲኖርበት 3ኛ ተጠሪን ጭምር ለጉዳቱ ሃላፊ ማድረጉ በግራ ቀኙ መካከል የተፈፀመውን ውል ያላገናዘበ ነው፣ለደረሰው ዘላቂ ጉዳት የ10 ዓመት ካሳ በተወሰነበት ሁኔታ እንደገና የ2 ዓመት ካሳ መወሰኑ ከጉዳት እና ካሳ ተመጣጣኝነት መርህ አኳያ አግባብነት፣1ኛ ተጠሪ ብር 288,000 (ሁለት መቶ ሰማንያ ስምንት ሺህ) የ10 ዓመት ካሳ በሚል ጠይቀው 312,550 ብር መወሰኑ አጠቃላይ የጠየቁት የካሳ ገንዘብ 488,000 (አራት መቶ ሰማን ስምንት) ከመሆኑ

አኳያ ባልተጠየቀ ዳኝነት ሊባል የሚችል አይደለም በማለት 1ኛ ተጠሪ ላይ ለደረሰው ጉዳት ካሳ መክፈል ያለበት አመልካች ነው ሲል የሥር ፍ/ቤት ውሳኔን በማሻሻል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን በመጥቀስ ለዚህ ችሎት የሰበር አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡በአመልካች የቀረበው የሰበር አቤቱታ ይዘትም በአጭሩ ከውል ውጭ ለሚደርስ ኃላፊነት የጉዳት ካሳ ጥያቄ በ2 ዓመት ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ የሚታገድ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ ከሰኔ 2008 ዓ.ም ጀምሮ ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑን በመግለፅ የጉዳት ካሳ የጠየቁት ታህሳስ 14 ቀን 2012 ዓ.ም በመሆኑ መብት ከነበራቸው እንኳን በመብታቸው መጠቀም የሚገባቸው በ2 ዓመት ጊዜ ውስጥ ባለመጠቀማቸው በፍ/ብ/ህ/ቁ 2143 ክሳቸው በይርጋ ቀሪ እንደሚሆን የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 119563 በቅፅ 20 ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ካሳ ከጉዳት ጋር የተመጣጠነ መሆን እንዳለበት የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥሮች 2090 እና 2091 ተደንግጎ እያለ እና 1ኛ ተጠሪ የጠየቁትን መሠረት ባደረገ መልኩ መወሰን ሲኖርበት ከጠየቁት በላይ አመልካች እንድከፍል መወሰኑ አግባብ አይደለም፡፡እንዲሁም ጉዳት ሊደርስ እንደሚችል በመገመት ጉዳቱ ከመድረሱ ከ6 ወር በፊት አመልካች 3ኛ ተጠሪን መሬት ያስለቅቅልኝ ጥያቄ አስቀድሜ በመጠየቅ ግዴታዬን እንደተወጣሁ በማስረጃም በሰው ምስክሮችም ተረጋግጦ እያለ በ3ኛ ተጠሪም ጥያቄዬን ተቀብሎ በስር ፍ/ቤት 4ኛ ተጠሪ መሬቱን ነጻ እንዲያደርግ የጠየቀበት ሰነድ ቀርቦ ባለበት አመልካች አስቀድሜ በማወቅ የማስተካከያ እርምጃ መውሰዴና የዲዛይን ክለሳ በማድረግ በ3ኛ ተጠሪ ተወካይ እንዲጸድቅ እንዳደረግኩ የስር ፍ/ቤት ቢረጋገጥም  አመልካች ብቻውን የፍትሐ ብሔር ኃላፊነት አለበት የሚል የተሳሳተ ድምዳሜ ላይ መድረሱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው የሚል ነው፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም 2ኛ እና 4ኛ መልስ ሰጪዎችን በተመለከተ የስር ፍርድ ቤት ኃላፊነት የለባቸውም በሚል የተሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍበት ምክንያት በአመልካች አቤቱታ ያልቀረበበት በመሆኑ መልስ መስጠት ሳያስፈልጋቸው በአመልካች የተሠራው እና በ3ኛ ተጠሪ አማካሪ አማካኝነት የፀደቀው ዲዛይን በ1ኛ ተጠሪ ይዞታ በጎርፍ ጉዳት መድረሱን ምክንያት ስለመሆኑ እና ለጉዳቱ ምክንያት የተደረገው ውሃ ማፍሰሻ በዲዛይኑ የተካተተ አይደለም በማለት አመልካች ያነሱትን መከራከርያ እና የጉዳት መጠኑን በተመለከተ የስር ፍርድ የሰጠውን ውሳኔ ከክርክር አመራር እና ተገቢውን ጭብጥ ከመያዝ አንፃር ለመመርመር 1ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡

1ኛ ተጠሪ በመስከረም 25 ቀን 2017 ዓ.ም ባቀረቡት መልስ በአጭሩ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ህጉንና ማስረጃን መሰረት ያደረገ በመሆኑ የሚነቀፍ አይደለም በሚል የቀረበው የሰበር አቤቱታ ውድቅ ተደርጎ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ እንዲፀናልኝ በሚል ተከራክረዋል፡፡

3ኛ ተጠሪም መስከረም 2 ቀን 2017 ዓ.ም በሰጡት መልስ ከአመልካች ጋር ባለን የግንባታ ውል አመልካች የዲዛይን፣የሰርቬይ እና የግንባታ እቃዎች ግዢ ስራ አጠቃሎ የመስራት ግዴታ፤በዚህም መሰረት አመልካች

ከሚሰራው ግንባታ ጋር ተያይዞ ለሚመጣ ማንኛውም ውድመት እና ኪሳራ ኃላፊት ያለበት ስለመሆኑ የሚጠቅስ ነው፡፡ጉዳቱ የደረሰው ከመሬት ማስለቀቅ ጋር ተያይዞ ሳይሆን አመልካች ከዲዛይን ጋር ተያይዞ በሰራው ጥፋት ነው፡፡ይህም ከድልድዩ የሚወጣውን ፍሳሽ ማስወገጃ ቦይ ባለመስራቱ ነው፡፡3ኛ ተጠሪ ከአመልካች ጋር በመሆን ዲዛይን የመስራትም ሆነ የማፅደቅ ግዴታ በመካከላችን በተደረገው ውል ላይ አልተሰጠውም፡፡በተጨማሪም ምንም አይነት የተፅዕኖ ግምገማ ስራ አይሰራም፡፡2ኛ ተጠሪ ምንም አይነት የግንባታም ሆነ የዲዛይን ስራ ስለማይሰራ በቀረበበት ጉዳይ ጥፋት ሳይፈፅም ኃላፊ የሚሆንበት አግባብ የለም፡፡እንዲሁም በዲዛይኑ ምክንያት ጉዳት ሳይደርስ በፊት ያቀረቡት የመሬት ይለቀቅልኝ ጥያቄ ባይኖርም ጉዳት ከደረሰም በኃላ ይኸው ጥያቄ ቢቀርብ እንኳን ጉዳዩ የሚታየው መሬትን በተመለከተ ከተደነገገው የህገ መንግስት ድንጋጌ አንፃር ሲሆን ከዚህ አንፃር አመልካች ያነሱት ክርክር ከህገ መንግስቱ ጋር የሚጣረስ ነው ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

አመልካችም 1ኛ ተጠሪ ላቀረቡት መልስ በህዳር 16 ቀን 2017 እንዲሁም 2ኛ ተጠሪ ላቀረቡት መልስ ደግሞ በጥቅምት 7 ቀን 2017 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጠናክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና የግራ ቀኙ ክርክር በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን እኛም አቤቱታ ከቀረበበት የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡እንደመረመርነውም 2ኛ ተጠሪ በሚያካሂደው የባቡር መስመር ድልድይ ግንባታ መነሻነት በ1ኛ ተጠሪ መሬት ላይ በጎርፍ ጉዳት በመድረሱ አመልካች ለግንባታው ዋና ተቋራጭ በመሆኑ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት ያለበት ስለሆነ ካሳ ሊከፍል ይገባል የሚል ሲሆን አመልካች በበኩላቸው የግንባታው ዋና ተቋራጭ መሆናቸውንና 3ኛ ተጠሪን መሬት ያስለቅቅልኝ ጥያቄ አስቀድሜ በመጠየቅ ግዴታዬን በመወጣት የማስተካከያ እርምጃ የወሰድኩ ሆኖ እያለ የደረሰውን የጉዳት ካሳ እንዲከፍል መወሰኑ አላግባብ ነው፣የባቡር መስመር ድልድይ ግንባታው የዲዛይን ክለሳ በማድረግ በ3ኛ ተጠሪ ተወካይ እንዲጸድቅ እንዳደረኩ በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ቢሆንም አመልካች የደረሰውን ጉዳት ለመካስ ብቻውን ኃላፊነት አለበት የሚል የደረሰበት ድምዳሜ እንደዚሁም የተወሰነው የካሳ መጠን ከተጠየቀው ዳኝነት በላይ ስለሆነ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን ስለሚያሳይ ውሳኔው ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡ስለሆነም በ3ኛ ተጠሪ የበላይ ተቆጣጣሪነት እና በአመልካች ዋና ተቋራጭነት እንደዚሁም በ2ኛ ተጠሪ ንዑስ ተቋራጭነት በተሠራው ድልድይ መነሻነት በ1ኛ ተጠሪ መሬት ላይ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት ያለው ማን ነው፣ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት ያለው አካል ሊከፍል የሚገባው የካሳ መጠን ምን ያህል ነው የሚል ሊመረመር የሚገባ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

አመልካች ጉዳቱ ሊደርስ የቻለው የባቡር መንገድ ድልድዩ ሲሰራ 3ኛ ተጠሪ መሬቱን ባለማስለቀቁ ነው የሚል ሲሆን የመሬቱ አለመለቀቅ ከድልድዩ ግንባታ ስራ ጋር ተያይዞ ለጉዳቱ መነሻ ስለመሆኑ የሚያሳይ ነገር ስለመኖሩ በስር ፍርድ ቤት የቀረበ ነገር ባለመኖሩ በዚህ በኩል የቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

አይደለም፡፡ሆኖም የባቡር መንገድ ድልድዩ ዲዛይን በአመልካች የተሠራ ሲሆን ዲዛይኑ ሲሠራ የፍሳሽ ማስወገጃ አብሮ ያልተሠራለትና 3ኛ ተጠሪ በበኩላቸው የባቡር ድልድዩ ድዛይን በአመልካች ተሰርቶ ሲቀርብላቸው የፍሳሽ ማስወገጃ አብሮ ተሰርቶ እንዲቀርብ ማድረግ ሲገባቸው የቀረበውን ዲዛይን ያጸኑ መሆናቸውንና በአመልካች ተሠርቶ በ3ኛ ተጠሪ በጸደቀው ዲዛይን መሠረት ድልድዩ በመሠራቱ ጉዳት የደረሰ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤት ተረጋግጦ ባለበት ለደረሰው የጉዳት ካሳ ክፍያ ሁለቱም ሃላፊነቱን መሸከም ያለባቸው ሆኖ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ለደረሰው ጉዳት አመልካች ብቻውን ተጠያቂ ነው በሚል በክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ያሻሻለበት አላግባብ ነው ብለናል፡፡

በሌላም በኩል 1ኛ ተጠሪ ጉዳት ድርሶብኛል በሚል የጠየቁት የአስር ዓመት ጉዳት ካሳ ብር 288,000 (ሁለት መቶ ሰማንያ ስምንት) ሲሆን በስር ክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 375,060 (ሶስት መቶ ሰባ አምስት ሺ.ህ) ሲወስን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከተጠየቀው የዳኝነት መጠን በላይ ብር 488,000 (አራት መቶ ሰማን ስምንት) እንዲከፈል የተወሰነ ስለመሆኑ መረዳት የሚቻል ነው፡፡የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተከራካሪ ወገኖች በዝርዝር ባላቀረቡት ወይም በግልጽ ባላመለከቱት ጉዳይ ላይ ፍርድ መስጠት የማይችል ስለመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 182(2) ድንጋጌ እንደዚሁም በሰበር መ/ቁ 31547፣33945 እና ተመሳሳይ ውሳኔዎችም አስገዳጅ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡የካሳ አከፋፈልና ልክ በሚመለከት ከውል ውጪ በሆነ ኃላፊነት ለደረሰ ጉዳት እንዲከፈል የሚወሰን ካሳ በተቻለ መጠን ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ የሚመዛዘን መሆን ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 2090/1 እና 2091 ስር ተመልክቷል፡፡ስለሆነም 1ኛ ተጠሪ በአመልካች እና 3ኛ ተጠሪ ድርጊት ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸው ስለመሆኑ በመጥቀስ የብር 288,000 (ሁለት መቶ ሰማንያ ስምንት) ካሳ እንዲከፈላቸው ዳኝነት የጠየቁ ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ክርክር የሚያሳይ ሲሆን የሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የደረሰውን ጉዳት ከተጠየቀው ዳኝነት በላይ ብር 375,060 (ሶስት መቶ ሰባ አምስት ሺ.ህ) ሲወስን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከተጠየቀው ዳኝነት እንደዚሁም በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከተወሰነው የዳኝነት መጠን በላይ ብር 488,000 (አራት መቶ ሰማንያ ስምንት ሺ.ህ) እንዲከፈል የተሰጠው ውሳኔ አግባብነት ያላቸውን ህጎች እና አስገዳጅ የሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎችን ያላገናዘበ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሲጠቃለል የስር አማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለደረሰው ጉዳት ኃላፍነት ያለው አመልካች ብቻ ነው በሚል የተሰጠው ውሳኔ እንደዚሁም በ1ኛ ተጠሪ ከቀረበው ዳኝነት በላይ ካሳ እንዲከፈላቸው የተሰጠው ውሳኔ በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4)(ሽ) እና 10(1)(ሠ) መሠረት መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ውሳኔ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማ አያገለግልም!

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 0114062 ጥቅምት 13 ቀን 2016 ዓ.ም እንደዚሁም በሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 30455 ጥር 17 ቀን 2015 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1)(ለ) መሠረት ተሻሽለዋል፡፡

2. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች በ1ኛ ተጠሪ ላይ የደረሰውን የጉዳት ካሳ ብቻውን የመክፈል ኃላፊነት አለበት በሚል የተሰጠው ውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡

3. የሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች እና 3ኛ ተጠሪ የክርክር መነሻ ለሆነው የካሳ ጥያቄ ያልተነጣጠለ ኃላፊነት አላቸው በሚል የሰጠው የውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡

4. አመልካች እና 3ኛ ተጠሪ በ1ኛ ተጠሪ መሬት ላይ ለደረሰው ጉዳት ካሳ ብር 288,000 (ሁለት መቶ ሰማንያ ስምንት) ባልተነጣጠለ ኃላፊነት እንዲከፍሉ ተወስኗል፡፡

5. ከሃላፊነት እና ሊከፈል ከሚገባው የካሳ መጠን ውጭ ሌላው በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የውሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡

6. በዚህ መዝገብ ላይ ጥር 06 ቀን 2016 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡

7. ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት ክርክር ያወጡትን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ ተዘግቷል፣ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

**ማስታወሻ፡** - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 256580

ታህሳስ 21 ቀን 2017ዓ/ም

**ዳኞች ፡-ገበየሁ ፈለቀ**

**ደረጀ አያና**

**ደጀኔ አያንሳ**

**ኑረዲን ከድር**

**ብርሀኑ መንግስቱ**

**አመልካች ፡- ሆሆተ ፋብሪካ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ፡- ጠበቃ ደሱ ጨመዳ ቀረቡ**

**ተጠሪ ፡- ወ/ሮ ዘውዲቱ በዳሶ፡- ቀረቡ**

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የጉዳት ካሳና የተቋረጠ ጥቅምን የሚመለከት ነው፡፡ክርክሩ በተጀመረው በቢሾፍቱ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡በከሳሽ የቀረበው ክስ ይዘት በአጭሩ ከአመልካች ፋብሪካ በሚወጣው መርዛማ ጭስ ምክንያት የግል ንብረቴ የሆነውን የሆላንድ ጥጃ ግምቱ ብር 10,000.00 (አስር ሺ) እና የሆላንድ የወተት ላም ብር 170,000.00 (አንድ መቶ ሰባ ሺህ) መስከረም 06 ቀን 2014 ዓ.ም ጥጃዋ ወዲያውኑ ስትሞት ላሚቷ መጋቢት 22 ቀን 2014 ዓ.ም ሞታለች፡፡ስለሆነም የሆላንድ ላሟ ከነጥጃዋ የዋጋ ግምት በድምሩ ብር 180,000.00 (አንድ መቶ ሰማኒያ ሺህ ) የሚያወጡ ሲሆን ላሟ ከመታመሟ በፊት በቀን 27 ሊትር ወተት የምትሰጥ ሲሆን የአንድ ሊትር ወተት ዋጋ ብር 40 የሚሸጥ በመሆኑ በቀን ብር 1080 (አንድ ሺህ ሰማኒያ) ሲሆን በወር ብር 32,400 (ሰላሳ ሁለት ሺህ አራት መቶ ብር) ገቢ ሳገኝ የነበረ ሲሆን ላሟ ለሶስት ወር ከ 9 ቀናት ታማ ምርት በማቆም ስትታከም በነበረበት

ማሳ ታወሻ፡ - ይህ የ ሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነ ድ ለ ጥና ትና ምር ምር ሥራ ወይም ለ ግንዛቤ እ ን ጂ ለ ፍርድ አ ፈጻጸ ም ዓላ ማ አ ያ ገ ለ ግልም!

ያጣሁት ገቢ ብር 106,920.00 (አንድ መቶ ስድስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሃያ) ጨምሮ በአጠቃላይ ብር 286 920.00 (ሁለት መቶ ሰማኒያ ስድስት ሺ ዘጠኝ መቶ ሃያ  እንዲወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

ተጠሪም በሰጡት መልስ ፋብሪካው ሲቋቋም በአካባቢው ላይ ተጽዕኖ የማያደርስ ስለመሆኑ ተረጋግጦ ነው፣ የክርክር መነሻ የሆኑት ጥጃ የሞተችበት እና ላሚቷ የታመመችበት ጊዜ የአመልካች ፋብሪካ ስራ ያልጀመረ በመሆኑ ለላሞቹ ሞት ምክንያት የደረሰው ጉዳት ከፋብሪካው የወጣ ጭስ ሊሆን የማይችል በመሆኑ አመልካች ለተጠሪ ጥጃ እና ላም መሞት ኃላፊነት የለበትም፤ካሳ ለመክፈልም ሊገደድ አይችልም በሚል የቀረበው ክስ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቀዋል፡፡

ክርክሩ የቀረበለት የወረዳ ፍርድ ቤትም የአመልካች ፋብሪካ ከቤቱ አቅራቢያ እንዳለ፤ፋብሪከው ሳይመዘገብ ስራ እንደጀመረ፣ከፋብሪካው የሚወጣው ጭስ ከስታንዳርድ በታች መሆኑና ለላሚቷ እና ጥጃዋ መሞት በሰው ምስክር፣ከባለሙያ ከቀረበው የምስክርነት ቃል ሲታይ ከአመልካች ምስክሮች በተሻለ ሁኔታ ያስረዱ ስለመሆናቸው ተረጋግጧል በሚል አመልካች የላሚቷንና የጥጃዋን ግምት እንደዚሁም የተቋረጠ ገቢ በጠቅላላው ብር 249,235 (ሁለት መቶ አርባ ዘጠኝ ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ አምስት) ለተጠሪ እንዲከፍል በሚል ወስኗል፡፡

አመልካች በተሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታቸውን ለምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን በማከራከር የክርክር መነሻ የሆነችው ላም ከአመልካች ፋብሪካ በሚወጣው ጭስ ምክንያት የሞተች ስለመሆኑ በስር ወረዳ ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ሲሆን ጥጃዋ በተመለከተ ተወልዳ ወዲያውኑ የሞተች በመሆኑ ከፋብሪከው በሚወጣው ጭስ ምክንያት ነው የሚል የሚያስቸግር ነው በማለት የላሚቷን ግምት ብር 49,000 (አርባ ዘጠኝ ሺህ) እንደዚሁም ከላሚቷ ከሚገኝ የወተት ሺያጭ የተቋረጠ ገቢን በሚመለከት ብር 27,870 (ሃያ ሰባት ሺ ስምንት መቶ ሰባ) በአጠቃላይ ብር 76,780.00 (ሰባ ስድስት ሺህ ሰባት መቶ ሰማኒያ) እንዲከፍል በስር ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በተመሳሳይ መልኩ በክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተሰጠው ውሳኔ ላይ የይግባኝ አቤቱታቸውን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ተጠሪ ለላሚቷ መሞት ምክንያት ከአመልካች ፋብሪካ በሚወጣው መርዛማ ጭስ ምክንያት ስለመሆኑ በማስረጃ አላስረዱም፣ አመልካችም ለደረሰው ጉዳት ተጠያቂነት የለበትም በሚል በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ሽሮታል፡፡

ተጠሪም በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በሚል እንዲታረም ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ችሎቱም ግራ ቀኙን በማከራከር  አመልካች የፌዴራል የአካባቢ ተጽዕኖ ጥናት አዋጅ ቁጥር 299/1995 አንቀጽ 3(1) እና የኦሮሚያ አካባቢ ተጽእኖ ጥናት አውድ በቁጥር 176/2005 አንቀጽ 5/1

ተደንግጎ ያለውን ግዴታ በመጣስ የአካባቢ ተጽዕኖ ጥናት አድርጎ ፍቃድ ሳያገኝ ብክለት ሊያስከትል በሚችል ስራ ውስጥ መሳተፉ፣የተጠሪ ላም የአመልካች ፋብሪካ ያለ ስራ ፈቃድ ስራ በጀመረበት ጊዜ የታመመች መሆኗ፣የላሚቷ በሽታ ምልክት ከፋብሪካ በሚወጣ ጭስ ምክንያት ጋር የሚያያዝ መሆኑ በእንስሳት ጤና ባለሙያ የተገለጸ መሆኑ በሰውና በባለሙያ የሙያ ምስክርነት የተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ ከአመልካች ፋብሪካ የሚወጣው ጭስ ብክለት ስታንዳርድ ደረጃ በታች ሆኖ እያለ ስራ በመጀመሩ ምክንያት ስራ እንዲያቆም መደረጉ ሲታይ አመልካች ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ መሆኑንና የደረሰውን የጉዳት ካሳ እንዲከፍል መወሰኑ በአግባቡ መሆኑን በመጥቀስ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠውን ውሳኔ በመሻር በምስራቅ ሸዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ በአብላጫ ድምፅ አጽንቶታል፡፡

አመልካች በክልሉ የሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን በመጥቀስ እንዲታረም በሚል አቅርበዋል፡፡በአመልካች የቀረበው የሰበር አቤቱታ ይዘት በአጭሩ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ከወረዳ ፍ/ቤት ጀምሮ እስከ ጠቅላይ ፍ/ቤት ድረስ ለተደረገው ክርክር በጭብጥነት የተያዘው የተጠሪ ላም የሞተችው ከአመልካች ፋብሪካ በሚወጣው ጭስ ምክንያት ስለመሆኑ ተረጋግጧል ወይ የሚል ሲሆን የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአብላጫ ድምፅ በሰጠው ውሳኔ ለተጠሪ ላም መሞት አመልካችን ኃላፊ ያደረገው ከፋብሪካው በሚወጣው ጭስ ጉዳት መድረሱን አረጋግጦ ሳይሆን የአከባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ፈቃድ ሳያገኝ ስራ ጀምሯል በሚል ምክንያት ነው፡፡ተጠሪ ላም ሞተችብኝ በማለት ያቀረቡት የክልልና የፌዴራል አከባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ባደረጉት ሳይንሳዊ ምርመራ የፋብሪካው ጭስ ከስታንዳርድ በታችና ጉዳት የማያደርስ ስለመሆኑ ተረጋግጧል፣ለላምቷ መሞት ከአመልካች ፋብሪካ በሚወጣ ጭስ ምክንያት ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ተጨባጭ ማስረጃ ሳይቀርብ አመልካች ፈቃድ ሳያገኝ ስራ መጀመሩ የተጠሪን ላም በመርዛማ ጭስ እንዲትሞት አድርጓል በሚል የተደረሰበት ድምዳሜ ተቀባይነት የለውም፡፡የተጠሪ ላም በምን ምክንያት እንደሞተች የሚያሳይ ማስረጃ የሌለ መሆኑን የከተማ አስተዳደሩ ግብርና ክላስቴር ጽ/ቤት በደብዳቤ ለፍርድ ቤት አሳውቆ እያለ ለተጠሪ ላም ሞት ምክንያት ከአመልካች ፋብሪካ በሚወጣ ጭስ ምክንያት ነው በሚል ካሳ እንድንከፍል የተወሰነበት ተጠሪየማ ስረዳት ሸክም ባልተወጡበትና ማስረጃ በአግባቡ ሳመዘን በመሆኑ የተሰጠው ውሳኔ እንዲታረምልን የሚል ነው፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም ለተጠሪ ላም ሞት ምክንያት ከአመልካች የሚወጣ መርዛማ ጭስ ስለመሆኑ የማስረዳት ሸክም ያለበት ማነው፣አግባብነትና ተቀባይነት ያለው ማስረጃ የቱ ነው እንደዚሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች የሚያወጣው ጭስ ከስታንዳርድ በታች መሆኑን ሳያሳይ ሥራ የጀመረ በመሆኑ ሃላፊ ነው በማለት ከሰጠው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንጻር ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ ትእዛዝ ተሰጥቷል፡፡

ተጠሪም በጥቅምት 02 ቀን 2017 ዓ.ም የተፃፈ መልሳቸውን ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያስተላለፈው ውሳኔ የወሰነው ስለ ጭሱ ሁኔታ እና የከብቶቹ ሞት የሚያውቁ የዓይን እማኞችና ላሚቷን ሲያክማት የነበረ የእንስሳት ሐኪም የሰጡትን የምስክርነት ቃል ሰምቶ ነው፡፡በተለይም ሀኪሙ የሞቷ ምክንያት የአየሩ ብክለት በመተንፈሻ አካሏ እና በልቧ ላይ ያደረሰው ጫና መሆኑን በቃለ መሓላ አረጋግጦ ሙያዊ ምስክርነቱን ሰጥቷል፡፡በተጨማሪም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መንግስታዊ አካላት ላይ ለማጣራት በተሰጠው ትዕዛዝ የተለያየ መልስ ቢሰጥም ከድርጅቱ የሚመጣው ጭስ በዓይን ሊታይ የሚችል ከመሆኑም በላይ በተደጋጋሚ የአካባቢው በሚደርስበት የጤና ችግር ምክንያት በየጊዜው በሚቀርብ አቤቱታ ምክንያት እየተዘጋ መልሶ እየተከፈተ አሁንም በዚሁ ችግር ምክንያት ተዘግቶ የሚገኝ ነው፣የማስረዳት ሸክምን በተመከተ ተጠሪ በትክክል የሚያውቁትን የዓይን እና የባለሞያ ምክስክርነት አሰምቻለሁ፡፡የባለሙያ ማስረጃ የሚያስፈልገው ደግሞ በዓይን በማየት ወይም በስሜት ህዋሳት ለመለየት የሚያዳግት ነገር ሲኖር ብቻ ነው፡፡ለመገመት አስቸጋሪ ቢሆን እንኳን በፍ/ሥ/ሥ/ህ ቁጥር 272 መሰረት በቦታው ተገኝቶ ማጣራት ይቻላል፡፡አመልካች ፈቃድ ሳያገኝ ስራ መጀመሩ ፈቃድ እንዳይከለከል የሚሸሸው ነገር እንደነበረው የሚያስረዳ ሲሆን ያለፈቃድ ለጤና ቀውስ የሆነ ሥራ መስራት ትክክል እንዳልሆነ ግልጽ ለሆነ የአመልካችን ኃላፊነት በአግባቡ የሚያመለክት እንጂ አመልካች እንዳለው መብት አይደለም፡፡ሥራ ከተጀመረ በኋላ የሚገመግመው በትክክል ስራውን እየሠራ መሆኑን ለማየት እንጂ ያለፈቃድ መስራቱን ለማፅደቅ አይደለም፡፡አመልካች ስላስገጠመው መከላከያ መሳሪያ ምንም ማረጋገጫ አላቀረበም፡፡የተጠሪ የሰው ምስክሮች በስሜት ህዋሳት የተረዱትን ስለሚመሰክሩ አግባብነት የላቸውም የተባለውን በተመለከተ ጭሱ ወደ ላይ ወጥቶ ተመልሶ ግቢያችን ውስጥ እንደሚገባና ከኛ አልፎ አካባቢውን ሁሉ እንደሚበክል መስክረዋል፡፡ አመልካች ስለ ሐኪሙ ምስክርነት ግን ምንም ማለት አልቻለም፡፡ሌሎቹም የዓይን እማኞች ቢሆኑ የፌደራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የፋብሪካውን ጭስ በመለካት ጉዳት እንደማያደርስ ገልጿል ያለውም ምርምራውን ያደረገው አደጋው ከደረሰ ረጅም ጊዜ በኋላ ሲሆን አመልካች ሲመጣበት የጭስ ልቀቱን ቀንሶ ሊሆን የሚችልበት ዕድል ያለው በመሆኑ አደጋው የነበረው የጭስ ልቀት ምን ያህል እና ምን ዓይነት እንደነበረ ያላስረዳ በመሆኑ በክልል ሰበር ሰሚው ችሎት የተሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ በአመልካች የቀረበው ሰበር አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቀዋል፡፡

አመልካችም ህዳር 04 ቀን 2017 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልሳቸውን አቅርበው አቤቱታቸውን አጠናክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ፣ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እና ቅሬታው ለሰበር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ነጥብ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ በስር ወረዳ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ከአመልካች ፋብሪካ በሚወጣው መርዛማ ጭስ ምክንያት የክርክር መነሻ የሆነችው ላም የሞቱባቸው መሆኑን በመጥቀስ የጉዳት ካሳና ላሚ ስትታመም በነበረችበት ወቅት

የተቋረጠ ገቢ እንዲከፈላቸው የሚል ሲሆን አመልካች በበኩላቸው ለተጠሪ ላም መሞት ከአመልካች ፋብሪካ በሚወጣው ጭስ ምክንያት ስለመሆኑ በማስረጃ ሳይረጋገጥ የቀረበው ክስ ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚል ነው፡፡የስር ኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በፌደራል የአካባቢ ተጽዕኖ ጥናት አዋጅ ቁጥር 299/1999 አንቀጽ 3(1) እንደዚሁም በኦሮሚያ አካባቢ ተጽዕኖ ጥናት በአዋጅ ቁጥር 176/2005 አንቀጽ 5(1) መሠረት በተመሳሳይ መልኩ የአካባቢ ተጽዕኖ ጥናት የሚያስፈልገው ፕሮጀክት ፈቃድ እስኪያገኝ ድረስ ሥራ መጀመር የሚከለክል ስለመሆኑ የተደነገገ ሲሆን በፌደራል የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 300/1995 አንቀጽ 3(1) ስር በሌላ በኩል ማንኛውም ሰው ዝቅተኛውን የአካባቢ ብክለት ስታንዳርድ ደረጃ በማለፍ አካባቢውን መበከል የሌለበት መሆኑን፣አመልካች በተጠቀሱት አዋጆች መሠረት የአካባቢ የተጽዕኖ ግምገማ ሳያደርግ ስራ የጀመረ መሆኑ በአካባቢው ብክለት ላይ ተሳታፊ መሆኑን የሚያሳይ ነው፣ከተጠሪ ፋብሪካ ከሚወጣው መርዛማ ጭስ ምክንያት ጉዳት የደረሰ ስለመሆኑ በቀረቡት የሰው ምስክርና የባለሙያ ምስክርነት መሠረት በማድረግ ፍሬ ነገር የማጣራት እና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ መሆኑን ድምዳሜ ላይ በመድረስ አመልካች ለደረሰው ጉዳት ሃላፊነት አለበት በሚል ተወስኗል፡፡አመልካችም በበኩሉ ጉዳቱ ሊደርስ የቻለው ከፋብሪካው በሚወጣው መርዛማ ጭስ ምክንያት ስለመሆኑ ሳይረጋገጥ የጉዳት ካሳ እና የተቋረጠ ገቢ እንድንከፍል የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3)(ሀ) ላይ በግልጽ እንደተመለከተዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉን ዉሳኔዎች በማረም ላይ የተገደበ መሆኑን የሚደነግግ ነው፡፡የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሲሆን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታዉን ተቀብሎ በሰበር የማየት ስልጣን የሚኖረዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ ብይኑ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች፣የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ የሚቃረን ሲሆን እንዲሁም አግባብነት ያላቸውን ህግ በመጥቀስ ወይም ህግን ያላግባብ በመተርጎም የተሰጠ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሆኖ ጉዳዩም አገራዊ ፋይዳን የሚመለከት ሲሆን ብቻ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 10(1) (ሐ) እና (መ) ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡

በዚህ መሠረት አንድ ሰው በሌላው ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ሥራ ከሠራ ወይም በእጁ የያዘው ነገር በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ካደረሰ ኃላፊ ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ በፍ/ህግ አንቀጽ 2027(2) ስር የተደነገገ ሲሆን ላደረሰው ጉዳትም ተመዛዛኝ የሆነ ኪሳራ መክፈል ያለበት ስለመሆኑ በፍ/ህግ ቁጥር 2090 እና 20191 የተደነገገ ስለመሆኑ መረዳት የሚቻል ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ከአመልካች ፋብሪካ በሚወጣው ጭስ ምክንያት የክርክር መነሻ በሆነችው ላም ላይ ጉዳት ከማድረሱም በላይ ሞትን ያስከተለ መሆኑን በመጥቀስ የተቋረጠ ጥቅም እንደዚሁም ካሳ እንዲከፈላቸው ያቀረቡትን ክስ እና በአመልካች የተሰጠውን መልስ ሲታይ የተጠሪ ላም ከአመልካች ፋብሪካ በሚወጣ ጭስ ምክንያት በመታመሟ ተጠሪ ከላሟ ሲያገኙ የነበረው ጥቅም የተቋረጠ ስለመሆኑ እንደዚሁም ላሟ በመሞቷ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር መሠረት በማድረግ እና ማስረጃን በመመዘን አመልካች የተቋረጠ ጥቅም እና በላሟ መሞት ምክንያት ካሳ ሊከፈል የሚገባ ስለመሆኑ ድምዳሜ ላይ የደረሰበት በአግባቡ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም።

ስለሆነም አመልካች በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔም ሕገ መንግስቱን የሚቃረን፣አስቀድሞ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሚቃረን፣ጉዳዩ አገራዊ ፋይዳ አለው ሊባል የሚችል እንደዚሁም ፍትህን የሚያዛባ ጉልህ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ያልተገኘ በመሆኑ የተሰጠው ውሳኔ በአዋጁ አንቀጽ 2(4)(ሀ)(ሸ) እና 10(1)(ሐ) እና (መ) ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች አንፃር ሲታይ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም።በዚሁ መሰረት ተከታዩን ውሳኔ ተሰጥቷል።

## ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 437051 ታህሳስ 02 2016 ዓ.ም የስር ኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠውን ቤት ውሳኔ በመሻር በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት የሰጠው ውሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2012 አንቀጽ 9(1)(ሀ) መሠረት ጸንቷል።
2. አመልካችና ተጠሪ በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ።

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፣ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ፋ/ዘ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መ/ቁ 257607

ታህሳስ 24 ቀን 2017 ዓ/ም

ዳኞች - ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

ብርቅነሽ እሱባለዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች ፦ ወ/ሮ አያልነሽ ሚሻል - በሀዋሳ vc ቀርቡ

ተጠሪ ፦ የሰብአዊ መብት ኮሚሽን (ኢሰመኮ) ሀዋሳ ጽ/ቤት

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳዩ የስራ ስንብት (ቅነሳ) ውሳኔን ተከትሎ የቀረበ ክርክርን የሚመለከት ነዉ፡፡ ክርክሩ የተጀመረዉ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን መደበኛ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ላይ ሲሆን ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ ደግሞ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን የኮሚሽነሮች ጉባኤ ግንቦት 22 ቀን 2015 ዓ/ም በቃለጉባኤ ቁጥር 14/2015 የሰጠዉ አስተዳደራዊ ዉሳኔ እና ይግባኙ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 0200127 ታህሳስ 16 ቀን 2016 ዓ/ም የሰጠዉን ዉሳኔ በመቃወም አመልካች ጥር 07 ቀን 2016 ዓ/ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸዉ ነዉ፡፡

**ማስታወሻ፡** - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን የሰው ሀብት ልማት ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት በቁጥር ሰመኮ/ሠ/440/2015 ጥር 9/2015 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ የአሁን ኮሚሽኑ አዲስ መዋቅር አስጠንቶ ሰራተኞችን ወደ አዲሱ መዋቅር ለመመደብ ለሚወጡት የስራ ማስታወቂያዎች በማመልከት ለስራ መደቡ የሚሰጠውን ምዘና መውሰድና ከሌሎች ተወዳዳሪዎች የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ የሚጠበቅ ሲሆን የአሁን አመልካች ባመለከቱት የስራ መደብ ላይ ተወዳድረው ባመጡት ውጤት መሰረት በአዲሱ መዋቅር ውስጥ የስራ መደብ ማግኘት ስላልቻሉ ከየካቲት 01/2015 ዓ.ም ጀምሮ ከኮሚሽኑ ጋራ ያለዎት የስራ ግንኙነት ተቋርጧል በማለት የስንብት ደብዳቤ ጽፏል፡፡

አመልካች ለቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ባቀረቡት አቤቱታ ኮሚሽኑ የግዥና አስዳደር ባለሙያ ለመቅጠር ባወጣዉ ማስታወቅያ ተመዝግቤ ለፁሁፍ ፈተና በቀረብኩበት ወቅት አብረዉኝ ከሚፈተኑት መካከል ቆንጂት በዛብህ የተባሉ ተፈታኝ ወደ ፈተና አዳራሽ ወረቀት ይዘዉ በመግባት ከወረቀቱ ላይ መልስ ሲሰሩ የነበር በመሆኑ በወቅቱ ፈተኝ ለነበሩት ለአቶ ቤዛዪ ከበደ በሌላዋ ተፈተኝ መቅደስ ካህሳይ አማካኝነት የተነገራቸዉ ቢሆንም ፈታኙ ወረቁቱን ወደ ቦርሳ እንድታስገባ ብቻ በማድረግ ትኩረት ሳይሰጡ አልፈዉታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በቃል ፈተና ወቅት እኔን ለመጉዳ አግባብነት የሌላቸዉ ጥያቄዎች ሲያቀርቡ የነበር በመሆኑ የዉድድሩ ዉጤት አድሏዊ እና አግባብነት የሌለዉ በመሆኑ ዉድቅ ሊደረግ ይገባል በሚል ቅሬታቸውን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡

ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዉ የቀረበዉን ቅሬታ መርምሮ ተወዳዳሪዎች ፈተና በሚፈተኑበት ወቅት አላስፈላጊ የማጭበርበር ተግባር ለመከላከል ተገቢው ጥንቃቄ ያልተወሰደና በተለይም በተያዘው ጉዳይ የመጀመሪያው የፈተና ሂደት ላይ ቅሬታ ቀርቦበት እንዲደገም ከመደረጉ አንጻር ወረቀት ይዘው ወደፈተና አዳራሽ የገቡትን ተፈታኝ ጉዳይ የበለጠ ጥንቃቄ በመውሰድ ተገቢው ዕርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ የአሰራር ክፍተት የሚታይበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይሁንና ፈተና አደራሽ ዉስጥ ወረቀት ይዘዉ የገቡትን ቆንጂት የተባሉ ተፈታኝን በተመለከተ ተገቢዉ እርምጃ መወሰድ የነበረበት ቢሆንም በዚህ ምክንያት በቅሬታ አቅራቢዋ ላይ የደረሰ ጉዳት ስለመኖሩ የቀረበ ማስረጃ የሌለ በመሆኑ በስራ ክፍሉ የተሰጠዉ ዉሳኔ የሚነቀፍ አይደለም በማለት በአብላጭ ድምፅ የአመልካችን ቅሬታ ዉድቅ አድርጓል፡፡

በልዩነት ሀሳባቸውን ያስፈሩት የኮሚቴው አባላት በበኩላቸው የሰው ሃብት ሥራ ክፍል በፈተና አዳራሽ ውስጥ ምንም አይነት ወረቀት አለመግባቱን የማረጋገጥ ኃላፊነቱን ሳይወጣ ፈተናው እንዲጀመር ማድረጉ እና በወቅቱ የተገኘውን ወረቀት በመቀበል አስፈላጊውን እርምጃ

ከመውሰድ መቆጠቡ የአሰራር ስርዓቱን ጥርጣሬ ውስጥ የሚከት ከመሆኑም በላይ ለአድሎ የተጋለጠ እና በተፈታኞች አይን ገለልተኝነቱን የሚያሳጣ ነው፡፡ አመልካች ኮሚሽኑ እኩል የመወዳደር መብቴን አልጠበቀልኝም፤ አድሎ ተፈጽሟል በማለት ያቀረቡት ክርክርም አሳማኝ ነው፡፡ በተጨማሪም በተመረመረው የሰነድ ማስረጃ መሰረት አሸናፊዋ ያገኙት ነጥብ የመጨረሻ ዝቅተኛው ነጥብ ሆኖ እያለ በቃለ መጠይቅ ከፍተኛ ነጥብ በማምጣት የውድድሩ አሸናፊ መሆናቸው የውድድሩን ተአማኒነት ጥያቄ ውስጥ የሚጥለው ነው፡፡ ስለሆነም አባላጫው ድምጽ የደረሰበት መደምደሚያ ከኮሚሽኑ ለፍትህ እና እኩልነት ቁርጠኛ መሆን እሴት ጋር የማይጣጣም በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፡፡ በመሆኑም የሰው ሃብት ሥራ ክፍል ግልፅና ወጥነት ያለው የፈተና አሰጣጥ ስርዓት በመከተል ውድድሩ ወይም ፈተናው በድጋሚ የሚካሄድበትን መንገድ እንዲያመቻች ወይም ውድድሩን እንደ ዕድል ባለመቁጠር ቅሬታ አቅራቢዋን በመመሪያው መሰረት በሌላ ክፍት የሥራ መደብ የመወዳደር መብትን ሊያስጠብቅ ይገባል በማለት የልዩነት የውሳኔ ሃሳብ አስፍረዋል፡፡

አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝተዉ ለኢሰማኮ ምክትል ዋና ኮሚሽነር ለመደበኛ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ካቀረቡት ቅሬታ በተጨማሪ ኮሚሽኑ በወሊድ ፈቃድ ቤት በነበርኩበት ግዜ አመልካችን ለማሰናበት ካለዉ ፍላጎት የተነሳ የዉስጥ እና የዉጭ ማስታወቅያ አዉጥቶ ዉጤት ሳይገልፅ በድብቅ በተደረገዉ ሂደት በስራ መደቤ ላይ ሌላ ሰራተኛ መቅጠራቸዉ ተገቢነት የለዉም በማለት ቅሬታ ቢያቀርቡም የአመልካች ቅሬታ ዉድቅ ተደርጎ የኮሚሽኑ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ዉሳኔ በማፅናት ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

በመቀጠልም አመልካች ይግባኝ ለኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን የኮሚሽነሮች ጉባኤ ያቀረቡ ሲሆን ጉባኤው አስቀርቦ ጉዳዩን መርምሮ በሂደቱ ውስጥ የታየ የአሰራር ክፍተት ቢኖርም ወ/ሮ ቆንጂት በዛብህ የተመደቡበትን የቅጥር ሂደት እና ውጤት ለመቀየር በቂ አይደለም በማለት ውሳኔውን አጽንቷል፡፡

በዚህ አስተዳደራዊ ውሳኔ ላይ አመልካች ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱ ተጠሪ መ/ቤት የፈተናው ሂደት ኩረጃ እንደተፈፀመበት እያረጋገጠ በአመልካች ላይ ጉዳት አልደረሰም የማለቱን አግባብነት፤ እንዲሁም አመልካች ከስራ እንዲሰነበቱ የተወሰነበትን አግባብነት ለማጣራት በሚል ጭብጥ ይዞ በማስቀረብ ግራቀኙን ካከራከረ በኃላ ዉሳኔው ግድፈት የለበትም በማለት አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው። አመልካች በውሳኔው ተፈፀመ የሚሉትን መሠረታዊ የሕግ ስሕተት እና የጉዳዩን አመጣጥ በመዘርዘር ውሳኔው በተጠሪ የወጣውን መመርያ እና አሰራርን ያልተከተለ ነዉ ተብሎ በአመልካች ላይ የተሠጠው ሕገወጥ ስንብት መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ እንዲሻር ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል። ጉዳዩም በሰበር አጣሪ ችሎት ታይቶ ለሰበር ችሎቱ ተመርቷል።

የአመልካች የሰበር አቤቱታ እና የሰበር አጣሪ ችሎቱ ጉዳዩን የመራበት ትዕዛዝ ተመርምሮ አመልካች በተጠሪ መስርያ ቤት ሲሰሩ ተጠሪ መስርያ ቤት በአዲስ አደረጃጀት መዋቅሩ ምክንያት ሰራተኞችን በፈተና አወዳድሮ ሲደለድል አመልካች የቀረበላቸዉን ፈተና አላለፉም በማለት ከሚሰሩበት መደብ ወደ ሚመጥናቸዉ የስራ መደብ ባለማዛወር ከስራ እንዲሰናበቱ የኮሚሽኑ የሰዉ ሀብት አስተዳደር የሰጠዉ ዉሳኔ በየደረጃዉ የሚገኙ ኮሚቴዎች በማፅናት ሲወስኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱም ይህን ዉሳኔ በማፅናት የሰጠዉን ዉሳኔ አግባብነት ተጠሪ መስርያ ቤት ለአዲስ እንዲደራጅ ካወጣዉ መመርያ ቁጥር 1/2013 አንቀፅ 9(ሀ) አንፃር አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ ታዞ ነሐሴ 06 ቀን 2016ዓ/ም የተፃፈ መልስ አቅርቧል።

የተጠሪ መልስ ይዘት ባጭሩ አመልካች በማናቸውም ሁኔታ ተጠሪ ተመጣጣኝነት ባለው የሥራ መደብ ላይ በራሱ ወይም በሌላ መሥሪያ ቤት ሊያስመድበኝ ይገባል ብለው ያቀረቡት ክርክር በስር ቅሬታ ሰሚ አካል ፊት ያላቀረቡት አዲስ አቤቱታ በመሆኑ በሰበር ሰሚ ችሎት መታየት የለበትም። በተጠሪ ተቋም አዲሱን መዋቅር ተግባራዊ ለማድረግ በወጣው መምሪያ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 5.4 እንደተደነገገው ሠራተኛው ለአዲሱ ሥራ መደብ የሚመደበው ውድድርን መሠረት ባደረግ የቅጥር ሂደት ሲሆን የሥራ መደቦች ዝርዝር እና ተፈላጊ ችሎታ ለሁሉም ሠራተኞች ተደራሽ እንዲሆን የተደረገ ሲሆን አመልካችም አዲሱን መዋቅር ተግባራዊ ለማድረግ በወጣው መመሪያ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 5.6. መሠረት የተቀመጠውን መስፈርት አሟላለሁ ብለው በመረጡት ሦስት የሥራ መደቦች ላይ የተወዳደሩ ሲሆን አመልካች በተወዳደሩባቸው የሥራ መደቦች የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ ባለመቻላቸው መመደብ አልቻሉም። ልዩ ቅጥርን የሚፈልግ አጋጣሚ ካልተፈጠረ በስተቀር በተጠሪ ተቋም መመሪያዎች መሠረት ያለውድድር በቀጥታ ወደ ማንኛውም የሥራ መደብ የሚመደቡበት ሁኔታ የሌለ በመሆኑ የአመልካች ቅሬታ ተቀባይነት የለዉም ተብሎ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክሯል። አመልካችም ክርክራቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን በበኩላችን የግራ ቀኙን ክርክር ከተያዘው ጭብጥ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደሚቻለው አመልካች የግዥና አስዳደር ባለሙያ ለመቅጠር በወጣዉ ማስታወቅያ ተመዝግበው ለፁሁፍና ለቃል ፈተና በቀረቡበት ወቅት ተከሰተ የሚሉትን ግድፈት በማንሳት ውድድሩ እና የዉድድሩ ዉጤት አድሏዊ እና አግባብነት የሌለዉ በመሆኑ ዉድቅ እንዲደረግ የሚከራከሩ ቢሆንም የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዉ በአብላጫ ድምጽም ቢሆን ተወዳዳሪዎች ፈተና በሚፈተኑበት ወቅት አላስፈላጊ የማጭበርበር ተግባር ለመከላከል ተገቢው ጥንቃቄ አለመደረጉን፣ በተለይም በተያዘው ጉዳይ የመጀመሪያው የፈተና ሂደት ላይ ቅሬታ ቀርቦበት እንዲደገም ከመደረጉ አንጻር ወረቀት ይዘው ወደፈተና አዳራሽ የገቡትን (በኃላም የውድድሩ አሸናፊ ተባሉትን) ተፈታኝ ጉዳይ የበለጠ ጥንቃቄ በመውሰድ ተገቢው ዕርምጃ አለመወሰዱ ስህተት ቢሆንም በዚህ ምክንያት በአመልካች ላይ የደረሰ ጉዳት ስለመኖሩ በማስረጃ አልረጋገጠም የሚል የፍሬ ነገር መደምደሚያ ላይ ተደርሷል፡፡ ይህ መደምደሚያ እስከላይኛው የኮሚሽነሮች ጉባኤ እና ይግባኝ ሰሚው የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት ድረስ ተቀባይነት ማግኘቱን ተገንዝበናል፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በህገ መንግስቱ አንቀጽ 80(3)(ሀ) እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 ከተሰጠው ስልጣን አንፃር የፍሬ ነገር ክርክሩን በድጋሚ መዝና የተለየ መደምደሚያ ላይ ለመድረስ የሚያስችለው ህጋዊ ስልጣን የለውም፡፡ ስለሆነም አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡት ቅሬታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪ ተቋም የፈተናው አሰጣጥ ግድፈት እንደነበረበት ከተቀበለው ለአመልካች ሌላ የፈተና ዕድል መንፈጉ፣ በአዲስ አደረጃጀት ሰራተኞችን አወዳድሮ ሲደለድል አመልካች ፈተና አላለፉም በማለት ከሚሰሩበት መደብ ወደ ሚመጥናቸዉ የስራ መደብ ባለማዛወር ከስራ እንዲሰናበቱ መወሰኑ፣ እንዲሁም ከሥራ የሚቀነሱ ቢሆን ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ስማቸውን በማስተላለፍ የሚመደቡበትን ሁኔታ አለማመቻቸቱ  ተቋሙ ለአዲስ አደረጃጀት ካወጣዉ መመርያ ቁጥር 1/2013 እና ተገቢነት ካላቸው ሌሎች ድንጋጌዎች አንፃር በአግባቡ ሊታይ ይገባል፡፡ ተጠሪ በዚህ ረገድ ባቀረበው መልስ አመልካች በማናቸውም ሁኔታ ተመጣጣኝነት ባለው የሥራ መደብ ላይ ተጠሪ በራሱ ወይም በሌላ መሥሪያ ቤት ሊያስመድበኝ ይገባል በሚል ወይም ተመሳሳይ ክርክር በስር ያላቀረቡ በመሆኑ መታየት የለበትም በማለት የተከራከረ ቢሆንም አመልካች አላግባብ በውድድሩ አሸናፊ ሳይደረጉ መቅረታቸውን እና ተጠሪ ያሳለፈው ውሳኔ መመሪያውን መሰረት ያደረገ ስላለመሆኑ በማንሳት ክርክራቸውን ሲያቀርቡ እንደነበር የውሳኔው ግልባጭ የሚያሳይ

በመሆኑና በጉዳዩ ላይ የመመሪያውን እና ተገቢነት ያላቸውን ህጎች ይዘት ተመልክቶ ውሳኔ መስጠት በየደረጃው ጉዳዩን በመመልከት ውሳኔ ከሰጡት አካላት የሚጠበቅና ክርክሩም የመመሪያውን ይዘት የሚመለከት የህግ ጉዳይ በመሆኑ ተጠሪ በዚህ ረገድ ያቀረቡት መከራከሪያ ተቀባይነት የለውም፡፡

በሌላ በኩል የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን አዲሱን አደረጃጀት ተግባራዊ ለማድረግ ያዘጋጀው እና ከሐምሌ 1/2013 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ በተደረገው መመሪያ አንቀጽ 9 የፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ የሰራተኛ ቅነሳን (ስንብትን) የሚመለከቱ አንቀጾች ተፈፃሚነትን የሚመለከት ዝርዝር ድንጋጌ ይዟል፡፡ በአንቀጹ ሥር እንደተደነገገው፡-

- በተሻሻለው የኮሚሽኑ አዋጅ ቁጥር 1224/2012 መሰረት የፌ/የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽንና ሰራተኞቹ ላይ ተፈፃሚነት የለውም፤
- ነገር ግን ቀደም ሲል በፌዴራል የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ መሰረት የተቀጠሩትን የኮሚሽኑን ሰራተኞች ጥቅም ለማስጠበቅ የአዋጁ የሰራተኛን ቅነሳ የሚመለከተው ክፍል ጥቅም ላይ ይውላል፤
- በመንግስት ሰራተኞች አዋጅ መሰረት ሰራተኛው ከስራ ሊቀነስ የሚችለው የስራ መደቡ ሲሰረዝ፤ መ/ቤቱ ሲዘጋ ወይም ትርፍ የሰው ኃል ሲኖር ነው፤
- በፌ/የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ አንቀጽ 30(1) መሰረት የመንግስት መ/ቤት አዲስ አደረጃጀት አጥንቶ ተግባራዊ ሲያደርግ ሰራተኞቹን በማወዳደር ደልድሎ ማሰራት ያለበት ቢሆንም በመ/ቤቱ ሰራተኛውን ለመደልደል ካልተቻለ ወይም ሰራተኛው ዝቅ ባለ ደረጃ ላይ ለመስራት ፈቃደኛ ካልሆነ ከስራ ይሰናበታል፤
- የመንግስት ሰራተኛ ቅነሳ የሚደረገው የመንግስት ወራተኛው በመ/ቤቱ ውስጥ በተመሳሳይ የስራ መደብ ላይ ካሉ ሌሎች የመንግስት ሰራተኞች ጋር ሲወዳደር በሥራ ውጤቱና ባለው ችሎታ ዝቅተኛ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፤ እንዲሁም
- ነፍሰ ጡር ሴት ሰራተኛ ወይም ወሊድ ፈቃድ ላይ ያሉ ሰራተኛ በቅነሳው ላይካተቱ እንደሚችሉ ይደነግጋል፡፡

ከዚህም ሌላ ቦታ ያላገኙ (ትርፍ የሆነ ሰራተኛን) በተመለከተ በመመሪያው አንቀጽ 11 ስር እንደተመለከተው፡-

- አዲስ መዋቅር በሚተገበርበት ጊዜ ቦታ ያላገኙ/ትርፍ የሰው ኃል አያያዝ ወይም አስተዳደር ቁልፍ ጉዳይ በመሆኑ በጥንቃቄ መያዝ እንዳለበት፤
- የተቋሙ የሰው ኃብት ድርሻም በሌላ መንግስት መስሪያ ቤት የሥራ ዕድል በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በኩል እንዲመቻችላቸው ቦታ ያላገኙ/ትርፍ የሆኑ ሰራተኞችን ዝርዝር መላክ ያለበት መሆኑን (አንቀፅ 11(1)(4))
- በሌላ መስሪያ ቤት እስከሚመደቡ ድረስ የሚኖረውን ክፍተት ለመሸፈን ደመወዝ ሊከፈል የሚችልበት ሁኔታ እና ጊዜውን የተመለከቱ ዝርዝር ድንጋጌዎች በመመሪያው ተካተዋል፡፡

ከፍሲል ከተጠቀሱት እና ተያያዥ የመመሪያው ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለው በፌዴራል የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ መሰረት የተቀጠሩትን የኮሚሽኑን ሰራተኞች ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል የፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 የሰራተኛን ቅነሳን የሚመለከተው ክፍል ለተጠሪ ተቋምም በተመሳሳይ ተፈፃሚ እንደሚሆን፤ ሰራተኞቹን በማወዳደር ደልድሎ ማሰራት ያለበት ቢሆንም በመ/ቤቱ ለመደልደል ካልተቻለ ወይም ሰራተኛው ዝቅ ባለ ደረጃ ላይ ለመስራት ፈቃደኛ ካልሆነ ከስራ እንደሚሰናበት፤ ሰራተኛው በመ/ቤቱ ውስጥ በተመሳሳይ የስራ መደብ ላይ ካሉ ሌሎች የመንግስት ሰራተኞች ጋር ሲወዳደር በሥራ ውጤቱና ባለው ችሎታ ዝቅተኛ መሆኑ ሲረጋገጥ የቅነሳ ጉዳይ የሚነሳ መሆኑን፤ ይህም ቢሆን ነፍሰ ጡር ሴቶች ወይም ወሊድ ፈቃድ ላይ ያሉ ላይካተቱ እንደሚችሉ ነው፡፡ ከዚህም ሌላ ቦታ ያላገኙ/ትርፍ የሰው ኃይል አያያዝ ወይም አስተዳደር ተገቢ ትኩረት ተሰጥቶት ሊሰራበት የሚገባ ጉዳይ ስለመሆኑም ከመመሪያው መረዳት ይቻላል፡፡

ይህ የአዋጁም ሆነ የመመሪያው ዓላማ በመ/ቤቱ በሚደረግ አዲስ አደረጃጀት ምክንያት ሰራተኛዉ የስራ ዋስትና እንዳያጣ ይልቁንም የሥራ ዋስትናው እንዲረጋገጥ የሚያደርግ ነው፡፤

በተያዘው ጉዳይ የተጠሪ የሰው ሃብት ሥራ ክፍል የፈተና አሰጣጥ ክፍተት ያለበት መሆኑና አመልካች እኩል የመወዳደር መብታቸው አለመጠበቁ ይልቁንም አድሎ ተፈጽሟል በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት የለውም ሊባል እንዳልቻለ ከስር ጀምሮ እስከ ኮሚሽነሮች ጉባኤ በየደረጃው ከተሰጡት ውሳኔዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህም ሆኖ በዚህ ምክንያት በአመልካች ላይ የደረሰ ጉዳት ስለመኖሩ የቀረበ ማስረጃ የለም ተብሎ መደምደሚያ ላይ የተደረሰበት ቢሆንም ከፍሲል ከጠቀስነው የተቋሙ መመሪያ እና ከአዋጁ ድንጋጌዎች አንጻር በመመልከት አመልካች የተሳተፉበትን ውድድር እንደ ዕድል ባለመቁጠር አመልካች በመመሪያው

መሰረት በሌላ ክፍት የሥራ መደብ የመወዳደር መብት እንዲጠበቅላቸው፤ ይህም ካልተቻለ አመልካች ዝቅ ባለ ደረጃ ላይ ለመስራት ፈቃደኛ ከሆኑ ዝቅ ባለ ደረጃ እንዲመደቡ አለመደረጉ፤ ይህ ሳይሆን ቀርቶ ከተቋሙ የሚሰናበቱ ከሆነም በሌላ መንግስት መስሪያ ቤት የሥራ ዕድል በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በኩል እንዲመቻችላቸው ለማድረግ ስማቸውን ማስተላለፍና በሂደቱም በህጉ የተፈቀደላቸውን መብት ማክበር ይገባል፡፡ ስለሆነም ጉዳዩ በዚህ አግባብ ሳይታይ በየደረጀው የተሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. አመልካች ባመለከቱት የስራ መደብ ላይ ተወዳድረው ባመጡት ውጤት መሰረት በአዲሱ መዋቅር ውስጥ የስራ መደብ ማግኘት አልቻሉም በሚል ከስራ እንዲሰናበቱ የተሰጠው ውሳኔ፤ እንዲሁም የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ሚያዚያ 9/2015 ዓ.ም በአብላጫ ድምጽ የሰጠው ውሳኔ፤ ምክትል ዋና ኮሚሽነር ግንቦት 4/2015 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ፤የኮሚሽነሮች ጉባኤ ግንቦት 22 ቀን 2015 ዓ/ም በቃለጉባኤ ቁጥር 14/2015 የሰጠዉ ዉሳኔ፤ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 0200127 ታህሳስ 16 ቀን 2016 ዓ/ም የሰጠዉን ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) እና በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1//ሀ/መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2. በሂደቱ የታየው የአሰራር ክፍተት ቢኖርም ወ/ሮ ቆንጂት በዛብህ የተመደቡበትን የቅጥር ሂደት እና ውጤት ለመቀየር የሚያስችል በማስረጃ የተረጋገጠ በቂ ምክንያት የለም ተብሎ በየደረጀው የተሰጠው ውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡

3. የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን አመልካች የተሳተፉበትን ውድድር እንደ ዕድል ባለመቁጠር አመልካች በመመሪያው መሰረት በሌላ ክፍት የሥራ መደብ የመወዳደር መብት እንዲጠበቅላቸው፤ ይህ ካልሆነም አመልካች ዝቅ ባለ ደረጃ ላይ ለመስራት ፈቃደኛ ከሆኑ ዝቅ ባለ ደረጃ እንዲመደቡ አለማድረጉ፤ ይህም ካልሆነ በሌላ የመንግስት መስሪያ ቤት የሥራ ዕድል በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በኩል እንዲመቻችላቸው አለመወሰኑ ክርክሩን እና በጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለውን መመሪያ እንዲሁም አዋጁን የተከተለ አይደለም ብለናል፡፡

4. የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን አመልካች በሌላ ክፍት የሥራ መደብ እንዲያወዳድር፤ ይህ በበቂ የህግ ምክንያት የማይቻል ከሆነና አመልካች ዝቅ ባለ ደረጃ ላይ ለመስራት ፈቃደኛ ከሆኑ ዝቅ ባለ ደረጃ እንዲመድብ፤ ይህም በበቂ የህግ ምክንያት ተፈጻሚ ማድረግ ካልተቻለ በሌላ መንግስት መስሪያ ቤት የሥራ ዕድል በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በኩል እንዲመቻችላቸው ስማቸውን እንዲያስተላልፍ፤ እንዲሁም በሂደቱ በህጉ የተፈቀደላቸውን መብት እንዲያከብር ወስነናል፡፡ የውሳኔው ግልባጭ ለኮሚሽኑ ይድረሰው፡፡

5. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡ ውሳኔው ጥር 14/2017 ዓ.ም በችሎት ተነቧል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 257723

ታህሳስ 25 ቀን 2017ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በእውቀት በላይ

መላኩ ካሳዬ

ማርታ ተካ

አየለ ማሞ

አመልካች፡- የወ/ሮ በላይነሽ ወንድማገኝሁ ወራሾች

1. አቶ በሻዳ ወርቁ ደፈሩ
2. አቶ ደበበ ወርቁ ደፈሩ

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ደበበ ቱሉ

2. አቶ መክበብ ቱሉ

3. አቶ አፈወርቅ ቱሉ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው የአመልካች ወራሾች ጥር 9 ቀን 2016 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 103926፤ ጥቅምት 15 ቀን 2016

ዓ/ም የሰጠው  ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 311281፡ ጥር 03 ቀን 2016 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የይዞታ ክርክር የሚመለከት ሲሆን ተጠሪዎች በአመልካቾች አውራሽ ላይ ክርክሩ በጀመረበት የፌደራል መጀመሪያ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘቱ ሲታይ፡- አመልካቾች በአዲስአበባ ከተማ አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ወረዳ 7 ሰርቲ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ ከነበራቸው ቦታ በምስራቅ መንገድ፣ በምእራብ የአቶ ደቻሳ መኖሪያ ቤት በሰሜን መንገድ፣ በደቡብ ኤሌክስቴራዞና እምነበረድ ፋብሪካ የሚያዋስኑት ስፋቱ 5057 ካሬ ሜትር ህዳር 1 ቀን 1984 ዓ.ም በተፃፈ የስጦታ ውል ለተጠሪዎች ያስተላለፉ መሆኑን፤ ተጠሪዎችም ለ30 ዓመት በ3ኛ ተጠሪ ስም ግብር በመገበር በእጃችን አድርገን አትክልቶችን በመትከልና በመዝራት የምናስተዳድረውን ይዞታ የአመልካቾች አውራሽ የሆኑት (ወ/ሮ በላይነሽ ወንድማገኝ)(ስር ተከሳሽ) መብትና ጥቅም ሳይኖራቸው ህጋዊ ይዞታችንን በጉልበት ነጥቀው የያዙ በመሆኑ ለቀው እንዲወጡ እንዲወሰንልን የሚል ነው፡፡

የአመልካቾች አውራሽ በቀን 22/06/2015 ዓ/ም በሰጡት መልስ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ይዞታ እና ሌሎች የእርሻ መሬቶች ከ1963 ዓ.ም ጀምሮ ከሟች ባለቤታቸዉ ጋር ተሰጥቷቸዉ ግብር እየገበሩበት በግብርና ስራ የሚተዳደሩበት ከእጃቸዉ ወጥቶ የማያወቅ ይዞታ ነው፡፡ ተጠሪዎች ሌሎች ወራሾች ባሉበት ሁኔታ ስጦታ ብለዉ ያቀረቡት ዉል የሀሰት ዉል እና ስለመደረጉም የማያዉቁት አዋሳኝ ያልተገለጸበት ነው፡፡ በስጦታ የሚተላለፈዉ ይዞታ የቱ እንደሆነ በፍ/ብሔርህግቁጥር 2443፣ ከ881 እስከ 883 ድረስ ባለዉ ድንጋጌ መሰረት ተሟልቶ ያልቀረበ እና በፍ/ብሔርህግቁጥር 1168 መሰረትም መብት የማይሰጣቸዉ ነው፡፡ በኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40(3) መሬት የመንግስትና የህዝብ መሆኑን የደነገገ በመሆኑ ዉሉ የተደረገበት የአርሶ አደር የእርሻ ይዞታ በስጦታም ይሁን በሽያጭ ማስተላለፍ ህገወጥ በመሆኑ ውሉ ተሰርዞ ወጪ ናኪሳራ የመጠየቅ መብቴ ተጠብቆ ይወሰንልኝ በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት ፍርድቤት አከራካሪው ይዞታ ተጠሪዎች በህጋዊ የስጦታ ውል ያገኙት እና በይዞታው ላይ ያሉ ተክሎችም የተጠሪዎች በመሆናቸው የአመልካቾች አውራሽ በህገወጥ መንገድ የያዙትን ለተጠሪዎች እንዲመልሱ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁን አመልካቾች የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት በሰጠው ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ቅሬታቸውን በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 337(1) መሰረት ሰርዟል፡፡

አመልካቾች በቀን 09/05/2016 ዓ/ም ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡት አቤቱታ አጭር ይዘቱም፡- በስር ፍርድ ቤት በተጠሪዎች የስጦታ ውል በሚል ያቀረቡት ሰነድ ዋናው ውል አልቀረበም፤ በፎቶ ኮፒው ውል ላይ ያለው ፊርማም የአውራሽም ሆነ የወራሾች ባለመኖኑ በፎረንሲክ እንዲመረመር ጠይቀን ተመርምሮ ሳይረጋገጥ፤ የስጦታ ውሉ ፎርማሊቲውን ያሟላ እንዳልሆነ ስጦታ ተሰጠ የተባለው ይዞታ በአዋሳኝ ተለይቶ የማይገልጽ ሆኖ እያለ፤ በባዶ መሬት ስጦታ መስጠትም ሆነ መሸጥ የማይቻል ስለመሆኑ በሰበር ችሎት በተለያዩ መዝገቦች ገዢ ውሳኔ የሰጠበት መሆኑን እንዲሁም በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 40(3)፣ በኢፌዲሪ ፌደሬሽን ምክርቤት መደበኛ ስብሰባ ሰኔ 15 ቀን 2007 ዓ.ም እና መጋቢት 3 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለው ስብሰባ አርሶአደርን ከይዞታው ማፈናቀልና ህገወጥ የአርሶአደር ይዞታን ማስተላለፍ ተፈፃሚነት እንደሌለው ውሳኔ የሰጠበት በመሆኑ በሥር ፍርድ ቤቶች የተጠሪዎች ክስ ውድቅ መደረግ ሲገባው አለመደረጉ እንዲሁም በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበርሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 79394 ቅፅ 14 ላይ ስጦታ ውሉ ህገወጥ ከሆነ ሌላ መዝገብ መክፈት ሳያስፈልግ በራሱ መዝገብ ታይቶ ውድቅ መደረግ እንዳለበት አስገዳጅ ውሳኔ ተሰጥቶም እያለ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠ ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ውሳኔዎቹ ተሽረዉ ይዞታው የአመልካቾች አውራሽ ነው ተብሎ እንዲወሰንልን የሚል ይዘት ያለው ነው።

የሰበር ችሎቱ ክርክር ያስነሳው ይዞታ ጥንት የአቶ ወርቁ ደፋር እንደነበረ በአሁኑ ሰአት የአመልካች ወራሾች ከሆኑት ውስጥ በአቶ በሻዳ ወርቁ እጅ እንደሚገኝና ከሟች አባቱ በውርስ ያገኘው ስለመሆኑ በወረዳው መሬት ልማት አስተዳደር ጽ/ቤት ተረጋግጦ እያለ ለአንድ ወገን ያደላ ማስረጃ ነው በሚል ባለመቀበል ይዞታው ተጠሪዎች በስጦታ ያገኙት ስለሆነ አመልካቾች ለቀው ሊያስረክቡ ይገባል በሚል መወሰኑ በሰ/መ/ቁ 44804፣229926፣229475 እና በሌሎች መዝገቦች ላይ ከማስረጃ ምዘና መርሆዎች አተገባበር አንጻር ከተሰጡ ውሳኔዎች አንጻር ለመመርመር እንዲሁም አመልካቾች ስጦታ ውሉን አናውቀውም ህጋዊ ውጤት ያለው አይደለም በሚል ያቀረቡት መከራከሪያ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ተጠሪዎች ባሉበት ለመመርመር ሲባል መልስ እንዲያቀርቡ ታዞ ግራቀኙ ክርክር አድርገውበታል።

ተጠሪዎች በቀን 25/07/2016 ዓ/ም የተጻፈ መልስ አቅርበዋል አጭር ይዘቱም፡-የአቤቱታው ምክንያት በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በአፈጻጸም መ.ቁ 111190 የተፈጸመና የአቤቱታው ምክንያት ቀሪ የሆነ በመሆኑ የአመልካች አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 280፣በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅጽ 9 ሰ.መ.ቁ 45371 እና በቅጽ 5 ሰ.መ.ቁ 27161 አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት አቤቱታው መዘጋት ወይም መሰረዝ ያለበት ነው። የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የቀረበለትን የሰነድ ማስረጃ ክብደትና ተዓማኒነት መዝኖ እውነቱ በተደበቀበት ጊዜ አጎራባችና አርሶአደር ኮሚቴ አባል በተከራካሪዎች ምስክር ዝርዝር

በምስክርነት መጠቀሳቸውን ተረድቶ ከሕጉ ጋር አዛምዶ መወሰኑ የማስረጃ ምዘና መርህን የተከተለ ነው፡፡ ስለስጦታው መኖር በውሉ በእማኝነት በፈረሙት የተረጋገጠና ውሉን አናውቀውም ህጋዊ ውጤት የለውም በሚል ክርክር የቀረበበት አግባብም የሥነሥርዓት ሕጉን ያልተከተለ ነው፡፡ ስጦታው በባዶ እርሻ መሬት ላይ ስላለመደረጉ በስር ፍ/ቤት በፍሬነገር ተረጋግጧል፡፡ የስጦታ ውሉ የተደረገው ህዳር ወር 1984 ዓ.ም ሲሆን ይህም የኢፌዲሪ ሕገመንግስት ከመጽደቁ በፊትና የፌዴሬሽን ምክርቤትም በሕገመንግስቱ ከመቋቋሙ በፊት የተሰጠ ስጦታ ውል በመሆኑ አመልካቾች የጠቀሱዋቸው የሰበር ውሳኔዎች ለዚህ ጉዳይ ተያያዥነት የሌላቸው ናቸው፡፡ በስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ ሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት በመሆኑ የአመልካቾች ሰበር አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እንዲፀናልን በሚል ተከራክረዋል፡፡ አመልካችቾም የሰበር አቤቱታቸውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርበው ክርክሩ በዚህ አግባብ ተጠቃሏል ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል፣ እኛም የቀረበውን ሰበር አቤቱታ፣ መልስ እና የመልስ መልሱን እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ እና ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን

መሠረት በማድረግ የሰበር ቅሬታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነዉም የሰበር ችሎቱ ስልጣን የመጨረሻ ዉሳኔ በተሰጠባቸዉ ጉዳዮች ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሞ ሲገኝ ይህንኑ በማረም የተገደበ ነዉ፡፡ የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ እና የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2/4/ እና 10 ይመለከቷል)፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 4 ስር ከሀ-ሸ እንደተዘረዘረዉ በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚችል የመጨረሻ ዉሳኔ፣ፍርድ፣ ብይን ወይም ትእዛዝ ላይ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን፣ ህግን አለ አግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉን ህግ የሚጠቅስ፣ለክርክሩ አግባብነት ያለዉ ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለዉ ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፣ በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ዉድቅ በማድረግ የተወሰነ፣ በፍርድ አፈጻጸም ሂደት ከዋና ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትእዛዝ የተሰጠበት፣ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተወሰነ፣የአስተዳደር አካል ወይም ተቋም ከህግ ዉጭ የሰጠዉ ዉሳኔ ወይም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ በመቃረን የተወሰነ ዉሳኔ ጉዳይ ስለመሆኑ ተደንግጓል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በተለያዩ መዛግብት ከሰጣቸዉ የሕግ ትርጉሞች መካከል አንዱ በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን እና በይግባኝ ሰሚነት የሚዳኙ ፍርድ ቤቶች የማስረጃ አቀራረብን፣ አግባብነትን፣ ተቀባይነትን እና ማስረጃ አቅርቦ አንድን ፍሬ ነገር የማስረዳት ሸክም የሚመለከቱ መርሆዎች አተገባበር በሚቃረን አኳኋን እንዲሁም የማስረጃ ምዘናን ወይም የማስረዳት ደረጃን የሚመለከቱ መሰረታዊ መርሆዎች በመጣስ የመጨረሻ ዉሳኔ መስጠታቸዉ በግልጽ ሲያረጋገጥ እንደመሰረታዊ የሕግ ስህተት ተቆጥሮ በፌዴራልም ሆነ በክልል ሰበር ሰሚ ችሎቶች ታይቶ ሊታረም እንደሚችል ነዉ፡፡ እንዲሁም በአንድ ማስረጃ ይዘት ላይ በግልጽ የተመለከተዉን በአግባቡ ያላገናዘበ ዉሳኔ መስጠት ወይም በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠዉን ነጥብ ከሕጉ ጋር ሳያገናዝቡ መወሰናቸዉ ከተረጋገጠ እነዚህን ስህተቶች በሰበር ችሎት ማረም ማስረጃ ወደ መመዘን ዉስጥ ተገብቷል የሚያስብል ሳይሆን እንደመሰረታዊ የሕግ ስህተት ሊቆጠርና በሰበር ሰሚ ችሎት ሥልጣን ማእቀፍ ዉስጥ ታይቶ ሊታረም ይገባል ሲል ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 44804 (ቅጽ 11 ላይ እንደታታተመዉ) ፣211615 (ያልታተመ)፣229926 (ያልታተመ) እና በሌሎች መዛግብት ላይ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

በያዝነው ጉዳይ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የሚቻለው ተጠሪዎች በስር ተከሳሽ በነበሩት የአሁኖቹ አመልካቾች አውራሽ እና አመልካቾች በኩል ህዳር 1 ቀን 1984 ዓ.ም በተፃፈ የስጦታ ውል አግኝተን ለ30 ዓመት በ3ኛ ተጠሪ ስም ግብር በመገበር በእጃችን በማድረግ አትክልቶችን በመትከል ስናስተዳድረው የነበረውን ይዞታ የአመልካቾች አውራሽ በሀይልና በጉልበት የያዙብን በመሆኑ ለቀው ያስረክቡን በሚል ያቀረቡት ክስ የአመልካቾች አውራሽ በኩል ለክሱ ምክንያት የሆነው መሬት ከ1963ዓ/ም ጀምሮ ከሟች ባለቤታቸው አቶ ወርቁ ደፋር ተሰጥቷቸው በግብርና ስራ ሲተዳደሩበት የነበረ የእርሻ መሬት መሆኑን ከባለቤታቸው ሞት በኃላም መሬቱን እያከራዩ ሲጠቀሙበት የነበረ ከእጃቸው ወጥቶ የማያውቅ መሆኑን፤ የስጦታ ውሉ እንደማያቁት፤ ውሉ የተደረገበት ጉዳይ ወይም የአርሶአደር የእርሻ መሬት በስጦታም ይሁን በሽያጭ ማስተላለፍ ህገወጥ ስለሆነና የውሉ አጻጻፍም በህጉ የተመለከተውን ፎርም ያልተከተለና በሚመለከተው አካል ያልተመዘገበ በመሆኑ ውሉ ህጋዊ ውጤት ያለው ባለመሆኑ ክሳቸው ውድቅ ሊሆን ይገባል በሚል መሆኑንና ፍርድ ቤቱም ተጠሪዎች ክርክር ያስነሳው የአርሶአደር መሬት ከአመልካቾችና አውራሻቸው በስጦታ ያገኙት ስለመሆኑ በምስክሮች ማስረዳታቸውን፤ የወረዳው መሬት ልማት አስተዳደር አርሶአደር ኮሚቴ ባገኘው መረጃ መሰረት ይዞታው ከጥንት የአመልካቾች አባት ሟች አቶ ወርቁ ደፋር እንደነበር፤ በአሁኑ ሰኣትም በ2ኛ አመልካች እጅ እንደሚገኝና ከአባቱ በውርስ ያገኘው መሆኑን ተገልጾ ምላሽ የቀረበ ቢሆንም ተጠሪዎች የማጣራቱን ሂደት ላይ ያቀረቡት ተቃውሞ ወደጎን በመተው በአመልካቾች በኩል ብቻ

የተነሳውን በመቀበል አጣርቶ ያቀረበው ሪፖርት ለአንድ ወገን ያደላ ነው በሚል ውድቅ በማድረግ ተጠሪዎች በይዞታው ላይ ቋሚ ተክሎች በመትከል ለ15 አመታት ግብር ያለማቋረጥ የገበሩ በመሆኑ የይዞታው ባለቤት ናቸው በማለት አመልካቾች በሀይልና በጉልበት የያዙት የተጠሪዎች ይዞታ ለቀው ሊያስረክቡ ይገባል በማለት መወሰኑን ይኸው ውሳኔ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በማጽናት ትእዛዝ መስጠቱን ነው፡፡

በዚህ ጉዳይ ተጠሪዎች በስጦታ በማግኘት ለረጅም አመታት ግብር በመክፈልና መሬቱን በማልማት ስንገለግበት የነበረውን መሬት የአመልካቾች አውራሽ በሀይል ስለተያዙ ለቀው ያስረክቡን በሚል ክስ ያቀረቡ ቢሆንም ይህ ጥያቄአቸው ምላሽ ሊያገኝ የሚችለው ተጠሪዎች የአከራካሪው ይዞታ ሕጋዊ ባለይዞታ መሆናቸው በቅድሚያ ሲረጋገጥ ነው፡፡

ተጠሪዎች በይዞታው ላይ መብት አገኘን የሚሉት ከአመልካቾች አውራሽ እና አመልካቾች በስጦታ ተሰጥቶናል በሚል ቢሆንም የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ልማት አስተዳደር በአርሶአደር ኮሚቴ ባደረገው ማጣራት ክርክር ያስነሳው የአርሶአደር መሬት የአመልካቾች አውራሽ የሆኑት አቶ ወርቁ ደፋር መሆኑንና በአሁኑ ሰአትም ልጃቸው በሆነው 2ኛ አመልካች እጅ እንደሚገኝና በውርስ ያገኘው መሬት መሆኑን ተረጋግጧል፤ተጠሪዎችም ቢሆኑ መሬቱ ከአመልካቾች አውራሽ እና አመልካቾች በስጦታ አግኝተናል በሚል ከሚከራከሩ በስተቀር ከመነሻውም ይዞታው የራሳችን ነው በሚል ያነሱት ክርክርም የለም፡፡ ሆኖም ስር ፍርድ ቤቱ ከሚመለከተው አካል ተጣርቶ የቀረበው ሪፖርት ውድቅ ለማድረግ የሚያስችል በቂ እና አሳማኝ የሆነ ምክንያት ሳይኖር ለአንድ ወገን ያደላ ማስረጃ ነው በሚል ይህም ቢሆን በድጋሚ ማጣራት ተደርጎ እንዲቀርብ ማድረግ ሲችል ከአርሶ አደሩ ኮሚቴ ተጣርቶ የቀረበው ማስረጃ፤ ለዚህ ማስረጃ ተገቢዉን ዋጋ ሰጥቶ ባለመመዘን ስጦታ ውሉ መኖር አለመኖር በሚመለከት የግራቀኙን ምስክሮች ቃልና የሰነድ ማስረጃ ብቻ መሰረት በማድረግ ተጠሪዎች በስጦታ ያገኙት ይዞታ አመልካቾች በሀይል መያዛቸው ተጠሪዎች ማስረዳታቸውን በተጨማሪም ከ15 አመታት በላይ ግብር መገበራቸውን ጠቅሶ አመልካቾች ይዞታውን ለተጠሪዎች ለቀው ያስረክቡ በሚል መወሰኑን ያሳያል፡፡ ይህም የስር ፍርድ ቤት የደረሰበት ድምዳሜ ከላይ እንደተጠቀሰው አከራካሪው ይዞታ የአመልካቾች አውራሽ መሆኑን በሚመለከተው አካል ተጣርቶ በማስረጃ የተረጋገጠው ፍሬ ነገር ያላገናዘበ ድምዳሜ በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ የማስረጃ ምዘና መርህ ጥሰት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል ፡፡

ከዚህም በተጨማሪ አመልካቾች የስጦታ ውሉ ህጋዊ ውጤት ሊያስገኝ የሚችል አይደለም በሚል በስርፍርድ ቤት ሰፊ መከራከሪያ አቅርበው ተከራክረዋል፡፡ የስጦታ ውሉ ህጋዊ መሆን አለመሆኑ ስንመለከት፡- በኢ.ፌ.ዴ.ሪ.ሕገ መንግስት አንቀጽ 40(3) መሰረት የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግስትና የሕዝብ ብቻ ነዉ፤ መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ

የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት ነዉ በማለት ደንግጓታል፡ ፡ከዛ በፊት ሀገሪቱ ስትመራ የነበረው በ1983 ዓ.ም በታወጀው የኢትዮጵያ የሽግግር ወቅት ቻርተር ሲሆን በቻርተሩ ስለመሬት ጉዳይ የተደነገገ ነገር ባይኖርም በአዋጅ ቁጥር 31/67 መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ መሆኑን ደንግጎ የሚገኝ በመሆኑ እና ይህም በሽግግር ወቅት በወጣው ቻርተሩ እስካልተሻረ ድረስ አዋጅ ቁጥር 31/67ም ሆነ አሁን በስራ ላይ ባለው ህገመንግስት መሬት መሸጥ የሚፈቅድ ህግ አልነበረም፡፡ ይህ ከሆነ አንድ ውል ደግሞ በሕግ ጥበቃ እንዲደረግለት ወይም እንዲጸና በሕጉ ተለይተው የተቀመጡት ሁኔታዎችን አሟልቶ ሊገኝ ይገባል፡፡ እነዚህ ሁኔታዎችም ውሉ ውል ለመዋዋል ችሎታ ባላቸው ሰዎች መካከል ጉድለት የሌለው ስምምነት መኖር፣ በቂ የሆነ እርግጠኛነት ያለውና ህጋዊ የሆነ ጉዳይ መሆንና የውሉ አጻጻፍ ፎርም በህግ በታዘዘ ጊዜ ይህኑ ልዩ ፎርም አሟልቶ መገኘት የሚሉትን ሶስት መሰረታዊ የሆኑ ሁኔታዎች ስለመሆናቸው የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1678 ድንጋጌው- ከሀ-ሐ ፊደላት ስር በዝርዝር አስቀምጧቸዋል፡፡ የቁጥሩ ፊደል "ለ" ድንጋጌ በተለይ ሲታይም ውሉ በቂ የሆነ እርግጠኛነት ያለውና ሕጋዊ የሆነ ጉዳይ ላይ መደረግ እንደሚገባው የሚያስገነዝበው ሲሆን በህግ እንዲደረግ ያልተፈቀደ፤ የሕግ ክልከላ ባለበት ጉዳይ ላይ የተደረገ ውል ደግሞ ሕገ ወጥ ውል ይሆናል፡፡ አንድ ውል የተደረገበት መሰረታዊ ጉዳይ በሕግ ክልከላ የተደረገበት በሆነ ጊዜም ውሉ በሕግ ፊት ምንም ዓይነት ህጋዊ ውጤት የማያስከትልና የማይጸና ነዉ፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አከራካሪው መሬት በከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ የእርሻ መሬት ሲሆን ተጠሪዎች ይህንኑ የእርሻ መሬት ከአመልካች አውራሽ እና አመልካቾች ህዳር 1 ቀን 1984 ዓ.ም በተደረገ ስጦታ ውል ያገኘነው ነው በሚል ቢከራከሩም አመልካቾች በኩል የስጦታ ውሉ አናውቀውም፤የአርሶ አደር የእርሻ መሬት በስጦታም ይሁን በሽያጭ ማስተላለፍ ህገወጥ ስለሆነና የውሉ አጻጻፍም በህጉ የተመለከተውን ፎርም ያልተከተለና በሚመለከተው አካል ያልተመዘገበ በመሆኑ ውሉ ህጋዊ ውጤት ያለው አደለም በሚል ተከራክረዋል፡፡ ይህ ሰበር ችሎትም አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት ይህንኑ ለማስረዳት ከክሳቸው ጋር በማስረጃነት አያይዘው ያቀረቡት የስጦታ ውል ይዘቱ ሲመለከት ስጦታ ሰጭዎች ለችግራቸው ማቃለያ የሚሆን ብር 5057(አምስት ሺህ አምሳ ሰባት ብር) ከስጦታ ተቀባዩቹ በመቀበል፤ 5057ካ.ሜ የሆነው ይዞታችን ለስጦታ ተቀባዮች በስጦታ ሰጥተናል የሚል እንደሆነ የውል ሰነዱ ከስር መዝገብ ጋር ተያይዞ ቀርቦ ለመመልከት ተችሏል፡፡ ይህ ከሆነ ርእሱ ሥጦታ ውል በሚል ሽፋን የአርሶአደር መሬት በተዘዋዋሪ በሽያጭ ለማስተላለፍ የተደረገ ስምምነት መሆኑን በቀላሉ መረዳት የሚቻል ነው፡፡ የከተማ መሬትን በተመለከተ መሬቱን የያዘ ሰው የመጠቀም መብት ከሚኖረው ውጭ የያዘውን ወይም ያገኘውን መሬት የመሸጥም ሆነ የመለወጥ መብት አይኖረውም፡፡

ይህ ታልፎ በመሬት ላይ የሚደረግ የሽያጭ ውል ህገ መንግሥቱም ሆነ ከዛ በፊት በሀገሪትዋ የነበሩ ህጎች የሚጻረር ውል በመሆኑ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ ፍርድ ቤቶች ህገ ወጥ የሆነ ውልን ተንተርሰው የሚመጡ ክርክሮችን በሌላ ተከራካሪ ወገን መቃወሚያ ባይቀርብበት እንኳን በራሳቸው በኩል አንስተው ክሱን ውድቅ ለማድረግ ይችላሉ፤ ከዚህ ጋር በተያያዘ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በህግ እንዲደረግ ያልተፈቀደ እና/ወይም የህግ ክልከላ ባለበት ጉዳይ ላይ የተደረገ ውል ህገ ወጥ ውል በመሆኑ ከመነሻው ውጤት የሌለውና ፈራሽ ስለመሆኑ በሰ/መ/ቁ.43226 የከቲት 7 ቀን 2003 ዓ/ም እንዲሁም በሰ/መ/ቁ. 79394 ጥቅምት 6 ቀን 2005 ዓ/ም አስገዳጅ ውሳኔ ሰጥቶበታል፡፡

በዚሁ ጉዳይም ክርክር ያስነሳዉን የመሬት ይዞታ ላይ ስጦታ ውል በሚል ሽፋን የተደረገው የሽያጭ ውል ስምምነት ከመነሻውም ዉሉ ሕገ-ወጥ በመሆኑ ተጠሪዎች ክርክር ያስነሳው ይዞታ ለማስለቀቅ መብት የሚሰጣቸው አይሆንም፡፡ ተጠሪዎች በሕገ-ወጥ ዉል መነሻነት በይዞታው ላይ ቋሚ አትክልቶችን አልምተዉበት ከሆነም በሌላ አግባብ ከሰው ከሚጠይቁ በቀር በይዞታው ላይ መብት አገኘንበት የሚሉት የስጦታ ውል ስምምነት ሰነድ ይዘቱ የመሬት ሽያጭ ውጤት ያለው ስምምነት በመሆኑ ከመነሻውም ውሉ ህጋዊ ውጤት አይኖረውም፡፡ እንዲሁም ተጠሪዎች ከመነሻውም ይዞታው ላይ ያቋቋሙት መብት ህጋዊ ውጤት በማያስገኝ ውል አመካኝነት በመሆኑ ይህን ተከትሎ በይዞታው ላይ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1168 መሰረት ለረዥም አመታት ግብር መገበራቸውም በይዞታው ላይ የባለይዞታነት መብት ሊያጎናጽፋቸው አይችልም፡፡

ሲጠቃለል ተጠሪዎች ከመሰረቱ ህገ ወጥ በሆነ ስጦታ ውል አመካኝነት መብት አቋቁሜያለሁ በሚል የአመልካቾች አውራሽ በሀይልና በጉልበት የያዙት ይዞታ ለቀው እንዲያስረክቡ በሚል ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ የውልን መፍረስ ዳኝነት ጥያቄ የሚጠብቅ ሳይሆን ፍርድ ቤቱ በራሱ በህገ ወጥ መንገድ የተገኘ የመሬት ይዞታ ጋር ተያይዞ የመጣ ክርክር በመሆኑ የሥጦታ ውሉ በተዘዋዋሪ የመሬት ሽያጭ ውጤት በሚያስከትል መልኩ ስምምነት የተደረገበት በመሆኑ በህግ ዘንድ ተቀባነይት የለውም በማለት ክርክሩን ውድቅ ማድረግ ሲገባው የስጦታ ውሉን እውቅና በመስጠትና ተጠሪዎች በዚሁ ህጋዊ ባልሆነ የውል ግንኙነት አመልካኝነት በይዞታው ላይ ለረዥም ጊዜ ግብር መገበራቸው የይዞታው ባለመብት ያደርጋቸዋል በማለት አመልካቾች ክርክር ያስነሳውን ይዞታ ለቀው ለተጠሪዎች ያስረክቡ በሚል የስር ፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መወሰኑም ሆነ ጉዳዩ በይግባኝ አለመታረሙ ከህግ አተገባበርም ሆነ ከማስረጃ ምዘና መርህ አንጻር ሲታይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 103926፣ ጥቅምት 15 ቀን 2016 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ፣ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 311281 ላይ ጥር 03 ቀን 2016 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9/1/ለ መሰረት ተሽሯል።
2. አመልካቾች ለክርክር መነሻ የሆነው ይዞታ ለተጠሪዎች ሊያስረክቡ አይገባም።
3. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል።

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

የሰ/መ/ቁ 257851
ታህሳስ 25 ቀን 2017ዓ/ም

ዳኞች፡-ገበየሁ ፈለቀ

ደረጀ አያና

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

ብርሃኑ መንግሥቱ

አመልካቾች፡-1ኛ. ፋጡማ ኢብራሂም

2ኛ. ኑሪያ ጅብሪል

3ኛ. አብዱለዚዝ መሀመድ

4ኛ. አብዱጀባር መሀመድ

5ኛ. ዘምዘም መሀመድ

ተጠሪ፡- መፍቱሃ ሙሳ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ጉዳዩ በፍርድ ቤት በተላላፈ ሰርኩላር(መመሪያ) መዝገብ ለጊዜው እንዲዘጋ የተሰጠን ትእዛዝ የሚመለከት ሲሆን ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣን በተመለከተው የምስራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካቾች የውርስ ድርሻቸውን እንዲታካፍላቸው በተጠሪ ላይ ክስ አቅርበው ክርክር ለመስማት ቀጠሮ በተያዘበት ቀን የአመልካቾች አድራሻ በሀረሪ ክልል ሀረር ከተማ ኤረር ቀበሌ ሲሆን የተጠሪ አዳራሻ ደግሞ ኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሐረርጌ ዞን ባቢሌ ወረዳ በመሆኑ በተለያየ ክልል

ነዋሪዎች መካካል የሚነሳ ክርክር መስተናገድ ያለበት በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ነው ወይስ በክልል ፍርድ ቤቶች የሚለው በፌዴሬሽን ምክር ቤት ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ ክርክሩ እንዲቆም የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት በቀጥር 3-228/838/15 ህዳር 30 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠውን ትዕዛዝ በመተላለፍ የግራ ቀኙን ክርክር ለመስማት ቀጠሮ መስጠቱ ስህተት በመሆኑ ስህተቱ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 208 መሠረት ታርሞ ጉዳዩ በፌዴሬሽን ምክር ቤት ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ ወይንም ተለዋጭ ትዕዛዝ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት እስከምሰጥ ድረስ ክርክሩ ባለበት እንዲቆም ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካቾች ይህን ትእዛዝ በመቃወም ባቀረቡት ይግባኝ አቤቱታ ጉዳዩን የተመለከተው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የምስራቅ ቋሚ ምድብ ችሎት ግራ ቀኙን አከራክሮ የምስራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ትዕዛዘ አጽንቷል፡፡

የሰበር ቅሬታ የቀረበው በየደረጃው ያሉ ጉዳዩን የተመለከቱት የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ትእዛዝ እና ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል በሰበር ለማሳረም ሆኖ የሰበር ቅሬታው ይዘት በአጭሩ፡- የምሰራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት መስከረም 4 ቀን 2016 ዓ.ም ክርክሩ ሊቀጥል አይገባም በሚል ቀርቦለት የነበረውን አቤቱታ ውደቅ ካደረገ በኋላ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉን ቁጥር 208 ድንጋጌን መሠረት አድርጎ ጥቅምት 12 ቀን 2016 ዓ.ም የቀረበውን ተመሳሳይ አቤቱታ በድጋሚ አይቶ አስቀድሞ የሰጠውን ትዕዛዝ መሻሩ፤ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት የፌዴራሽን ምክር ቤት የህግ ትርጉም እስኪሰጥ ድረስ ክርክሮች ታግደው እንዲቆዩ መመሪያ ያስተላለፈው በአዲስ አበባ ከተማ እና በኦሮሚያ ክልል ነዋሪ በሆኑ ተከራካሪዎች መካከል የሚደረገውን ክርክር የሚመለከት እንጅ በኦሮሚያ እና የሀረሪ ክልል ነዋሪዎችን የማይመለከት ሆኖ ሳለ የሰበር ሰሚ ችሎቱ የሰጠው ትዕዛዝ ተጠቅሶ ክርክሩ መቋረጡ፤የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት የክልል ያልሆነ(በፌደራል ጉዳይ) በመመሪያ የማስቆም ሥልጣን የለሌለው መሆኑ እየታወቀ መመሪያውን መሠረት አድርጎ መዝገቡ መዘጋቱ፤ ይግባኝ ሰሚው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ይህንኑ ትዕዛዝ ማጽናቱ በሕገ-መንግስቱ የተከበረላቸውን መብት የሚጥስ ስለሆነ የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ትእዛዝ እና ውሳኔ ተሽሮ መዝገቡ ከቆመበት ተንቀሳቅሶ ውሳኔ እንዲሰጥ ይወሰንልን የሚል ነው፡፡

በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 6/1 መሠረት ለሰበር ሰሚው ችሎቱ የተመራው የሰበር አቤቱታ በሰበር ሰሚ ችሎቱ ተመርምሮ የምሥራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት መስከረም 4 ቀን 2016 ዓ.ም የሰጠውን ትዕዛዝ ጥቅምት 12 ቀን 2016 ዓ.ም ማረሙ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 208ን አጠቃላይ መንፈስ እና ግብ ያገናዘበ መሆን አለመሆኑን፤የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሕዳር 30 ቀን 2015 ዓ.ም

የሰጠው ትዕዛዝ የዜጎችን በተፋጠነ ሥነ ሥርዓት ፍትሕ የማግኘት መብትን ያገናዘበ መሆን አለመሆኑን፤ሰበር ሰሚ ችሎቱ በፌደሬሽን ምክር ቤት የተያዘው ጉዳይ ተገቢው እልባት እስኪያገኝ ድረስ ክርክሮች በሙሉ ተቋርጠው እንዲቆዩ የማዘዝ ሥልጣን አለውን? አለው ከተባለስ ህዳር 30 ቀን 2015 ዓ.ም የተሰጠው ትዕዛዝ በሥር ፍርድ ቤት በተያዘው ክርክር የነዋሪዎች አድራሻ አንፃር ተመሳሳይ መሆን አለመሆኑ፤ውጤቱ ምን ሊሆን ይገባል የሚሉ ጭብጮችን ለማጣራት ተጠሪ መልስ እንዲሰጡ ታዘው ተከታዩን መልስ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ ለሰበር አቤቱታው በሰጡት መልስ፡- የምስራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቀድሞ መኖሩን ያልተረዳውን ወይም መኖሩ ያላወቀውን መመሪያ ወይም የሰበር ውሳኔ መሰረት አድርጎ ቀድሞ የሠጠውን ትእዛዝ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 208 መሠረት ማንሳቱ የራሱን ውሳኔ ቀይሯል ሊባል የማይችል መሆኑን፤ ክርክሩ ቀጥሎ ሊሰጥ ከሚችለው ውሳኔ ዋጋ አልባነት አንፃር ተገናዝቦ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈፀመበት መሆኑን፤የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎቱ መመሪያ ወይም የሰበር ውሳኔው ዓላማ የተከራካሪ ወገኖች የመኖሪያ አድራሻ ብቻ መሰረት በማድረግ በክልሉ ውስጥ የሚገኝ ንብረት አስመልክቶ የሚቀርብ ጉዳይን የመዳኘት ስልጣን ለፌደራል ፍርድ ቤቶች መሰጠቱ አግባብ ባለመሆኑ የክልሉን ሉዓላዊነት እንዳይነካ ለመጠበቅ ሲባል ማንኛውንም የሁለት ክልል ነዋሪዎችን የሚመለከት በመሆኑ ትዕዛዙ በተያዘው ጉዳይ ላይ ተፈፃሚነት የለውም በማለት የቀረበው የሰበር ቅሬታ የተሳሳተ ስለሆነ ተቀባይነት የለውም፡፡ የሰበር ሰሚ ችሎቱ ትዕዛዝ በኦሮሚያ ክልል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 216/2011 አንቀጽ 29/1 መሰረት በአምስት ዳኞች በሙሉ ድምጽ የተሰጠ የህግ ትርጉም በየደረጃው ባሉት የክልሉ ፍርድ ቤቶች ላይ አስገዳጅነት ስላለው ጉዳዩ በፌዴሬሽን ምክር ቤት ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ የተሰጠው ጊዜያዊ ትዕዛዝ የአመልካቾችን በፍርድ ቤት የመዳኘት እና ፍትሕ የማግኘት መብትን የሚገድብ አይደለም፡፡ የሰበር ቅሬታ ውደቅ ሆኖ ከበቂ ወጪ እና ኪሳራ ጋራ እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸውን የሚመስል ሲሆን እኛም ለሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነውን ትዕዛዝ እና ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመ መሆን አለመሆኑን የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ሲባል የተያዙ ጭብጦችን ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ፤እንዲሁም በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ ከተሰጠው የሰበር ውሳኔ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደምከተለው መርምረናል፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት በፌዴራል እና በክልሎች የተዋቀረ መሆኑ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐሊክ ሕገ መንግስት አዋጅ ቁጥር 1/1987 አንቀጽ 46(1) እና አንቀፅ 50(1) ሥር ተመልክቷል፡፡ የፌደራልም ሆነ የክልሎች ሥልጣን ምንጭ ሕገ-መንግስት መሆኑንና አንዳቸው የሌላኛቸውን ስልጣን ማክበር እንዳለባቸው አንቀጽ 50(8) ይደነግጋል፡፡ ለሁለቱም መንግስታት የተሰጠው ስልጣንም የህግ

አውጪነት፤የህግ አስፈፃሚነት እና የዳኝነት ስልጣን ስለመሆኑ በአንቀፅ 50/2 ስር ተመልክቷል፡፡ በዚህ መልኩ ለፌዴራል መንግስቱ የተሰጠው ስልጣን በህገ መንግስቱ አንቀፅ 51 ስር የተዘረዘረ ሲሆን ለክልሎች የተሰጠው ስልጣን ደግሞ በአንቀፅ 52 ስር በዝርዝር ተመልክቷል፡፡

በህገ መንግስቱ ለሁለቱም መንግስታት የተሰጠውን ስልጣን በጥቅሉ በሶስት ክፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው ለፌዴራል መንግስቱ ብቻ ተለይቶ የተሰጠ ስልጣን (Exclusive Federal Jurisdiction) ነው፡፡ ሁለተኛው ለክልል መንግስታት ብቻ ተለይቶ የተሰጠ ስልጣን (Exclusive Regional Jurisdiction) ሲሆን ሶስተኛው ደግሞ ለሁለቱም መንግስታት በጋራ የተሰጣቸው ስልጣን (Concurrent Jurisdiction) ነው፡፡ በህገ መንግስቱ ለክልል መንግስታት ከተሰጠው ስልጣን ውስጥ አንዱ በግልፅ ተለይቶ ለፌዴራል መንግስቱ ብቻ ወይም ለፌዴራል መንግስት እና ለክልል መንግስታት በጋራ ባልተሰጠ ጉዳይ ላይ ስለመሆኑ የህገ መንግስቱ አንቀፅ 52(1) ይደነግጋል፡፡

በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 78 መሠረት የዳኝነት አካሉ በፌዴራል እና በክልል መንግሥት ደረጃ መቋቋሙ እና በአንቀጽ 80/1 እና (2) ላይ በፌዴራል ጉዳዮች የፌዴራል ፍርድ ቤት፣ በክልላዊ ጉዳዮች የክልል ፍርድ ቤት የመጨረሻ ሥልጣን ያለው መሆኑ መመልከቱ በፌዴራልና በክልል መንግሥታት መካከል የፍርድ ቤት የሥልጣን ክፍፍል እንዳለ ያሳያል፡፡ የፌዴራል ወይም የክልል ጉዳዮች የሚለው በጉዳይ ዓይነት የተከፋፈለ ሥልጣን ስለሆነ የፍርድ ቤቶች ሥልጣን የተለየው የሥረ-ነገር ሥልጣንን መሠረት ያደረገ ቢመስልም ጉዳዩ ከሉዓላዊ ሥልጣን እና ክልላዊ ጉዳይ በፌዴራል ፍርድ ቤት ቢታይ ከጣልቃገብነት ጋር የሚያያዝ ነው፡፡ ሕገ-መንግሥቱ የፌዴራልና የክልል ፍርድ ቤቶች ያቋቋመና አንዱ የሌላውን ሥልጣን አክብረው ለማስከበርም ግዴታ የሚጥል ቢሆንም በፌዴራል መዋቅር የፌዴራል መንግሥት ሉዓላዊነቱ በመላው የኢትዮጵያ ግዛት ነው፡፡ ነገር ግን በግዛቱ ሥር ሁሉንም በፈቃዱ መወሰንና መፈጸም የሚችል ሳይሆን በግልጽ በሕግ በተዘረጋው ሥርዓት ሥልጣኑን የሚጠቀም መሆኑን የሚመለከት ነው፡፡

የዳኝነት አካሉ በፌደራል እና በክልል የተዋቀረ ቢሆንም፣ የፍርድ ቤቶቹ አደረጃጀት ትይዩ ባለመሆኑ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች በክልላቸው ከሚሰጧቸው የዳኝነት ሥልጣን በተጨማሪ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሥልጣንን በውክልና ደርበው የሚሰሩ ሲሆን፣የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶችም በክልላቸው ከሚኖራቸው የዳኝነት ሥልጣን በተጨማሪ በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሚታዩ ጉዳዮችን የማየት ሥልጣን አላቸው፡፡ (የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(2) እና 80(4) ይመለከቷል፡፡) በሕገ-መንግሥቱ የሥልጣን ክፍፍሉም የክልል ከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የፌዴራል ጉዳዮችን በውክልና ማየት የሚችሉ ሲሆን ክልላዊ ጉዳዮች በክልሎች ሉዓላዊ ሥልጣን ክልል ውስጥ (exclusive jurisdiction of state courts) ያለ በመሆኑ፣በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 80(3/ሀ) ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ሰሚ ችሎት የተሠጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የፌዴራል

ፍርድ ቤቶች የክልል ጉዳይን ማየት አይችሉም፡፡ ይሕም ክልላዊ ጉዳዮች ላይ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የመዳኘት ሥልጣን (judicial jurisdiction) የሌላቸው መሆኑን ሲያሳይ በውክልና እና በጣምራ ሥልጣናቸው ከሚመለከቱት በሥተቀር የክልል ፍርድ ቤቶች የፌዴራል ጉዳዮችን ማየት አይችሉም፡፡ የክልል ፍርድ ቤቶች በፌዴራል ፍርድ ቤት በብቸኝነት እንዲታዩ የተለዩ ጉዳዮችን (exclusive jurisdiction) በግዛታቸው በተከሠቱ ጉዳዮች፤ባሉ ሰዎች ወይም ንብረቶች ጋር የሚነሱ ሲሆን በውክልና (delegation) እንዲመለከቱ በሕገ-መንግሥት ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡ በሕገ-መንግሥቱ የዳኝነት አካል በፌዴራልና በክልል ደረጃ በየእርከኑ መዋቀሩ ሲታይ አደረጃጀቱ በተዋረድ ያለ የትይዩ አቀራረጽ (dual system) ያለው ቢሆንም የፌዴራል እና የክልል ጉዳዮችን የክልል ፍርድ ቤቶች መመልከታቸው የተደባለቀ (integrated system) እንደሚከተልም ያመለክታል፡፡

የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በክልሉ ጉዳይ ላይ የበላይ እና የመጨረሻ የዳኝነት ሥልጣን ያለው ሲሆን መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያሉበትን የክልል ጉዳዮችን በሰበር የማየት ሥልጣንም አለው፡፡ (የኢ.ፌ.ዲ. ሪ ሕገ-መንግሰት አዋጅ ቁጥር 1/1987 አንቀጽ 80/3(ለ)፤የተሸሻለው የኦሮሚያ ክልል ሕገ-መንግስት አዋጅ ቁጥር 46/1994 አንቀጽ 64/1(ሀ) እና (ሐ)፤የኦሮሚያ ክልል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 216/2011 ቁጥር 25/2(ረ)፤ እና 26 ድንጋጌዎችን ይመለከቷል፡፡) በዚህ አግባብ የተሰጠውን ሥልጣን ተግባራዊ ሲያደርግ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔን ማጽናት፤ማሻሻል ወይም መሻር እንደሚችል ከአዋጅ ቁጥር 216 ቁጥር 26/5 ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በፌዴራል እና በክልል ፍርድ ቤቶች መካከል በሕግ ግልጽ የሆነ የፍትሐ ብሔር ጉዳዮች የሥረ-ነገር ክፍፍል ባይኖርም የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 3 ድንጋጌ መሠረት የፌደራል ፍርድ ቤቶች ሕገ-መንግስቱን፤የፌደራል መንግስቱን ሕጎችና ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን መሠረት በማድረግ የሚነሱ ጉዳዮችን፤በፌደራሉ መንግስቱ ሕግ ተገልፀው በተወሰኑ ባለጉዳዮች እንዲሁም በፌደራል ሕገ-መንግስት ወይም በሕግ በተገለጹ ቦታዎች ላይ የዳኝነት ሥልጣን እንዳላቸው ይደነግጋል፡፡ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 4 እና 5 ሥር በተዘረዘሩት ጉዳዮች የፌዴራል ፍርድ ቤት በብቸኝነት ሥልጣኑ(exclusive jurisdiction of federal courts) የሚመለከታቸው ሕግንና ባለጉዳዮችን መሠረት አድርጎ የተለዩ የፌዴራል ጉዳዮች ሲሆን በሌሎች ሕጎች በግልፅ ለፌዴራል ፍርድ ቤት የተሠጡ ጉዳዮችንም ይጨምራል፡፡ የአዋጁን አንቀጽ 11 እና ተከታዮን ድንጋጌዎች ስንመለከት ደግሞ ቦታን መሠረት በማድረግ አዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተሞች ላይ የሚነሡ ጉዳዮች የፌዴራል ፍርድ ቤት የሚመለከታቸው የፌዴራል ጉዳዮች እንደሆኑ ተደንግጓል፡፡

የፌደራል እና የክልል ፍርድ ቤቶችን ጣምራ ሥልጣን በሚደነግገው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 80/4 የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በክልሉ ከሚኖረው የዳኝነት ስልጣን በተጨማሪ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣን ይኖረዋል በማለት ደንግጓል፡፡ የፌዴራል ፍርድ

**ማሳታወሻ፡** - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 3(1/ለ) ስር የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የወል የዳኝነት ስልጣን ይኖራቸዋል ተብለው ከተደነገጉ ጉዳዮች መካከል አንዱ የፌዴራል መንግስቱ ሕግ ተገልጸው በተወሰኑ ባለጉዳዮች መካከል የሚነሱ ክርክሮችን ተመልክቶ መወሰን የሚገኝበት ሲሆን የፌደራል ፍርድ ቤቶችን የፍትሐ ብሔር የወል የዳኝነት ሥልጣን የሚደነግገው የአዋጁ አንቀጽ 5(1/ሸ) ደግሞ መደበኛ ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች፤በክልል እና በአዲስ አበባ ከተማ፤በክልል እና በድሬዳዋ ከተማ፤ በአዲስ አበባ ወይም በድሬዳዋ ከተማ ዉስጥ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚነሱ የፍትሐብሔር ጉዳዮችን ተመልክቶ የመወሰን ስልጣን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን መሆኑ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በዚህ አዋጅ በተሻረው አዋጅ ቁጥር 25/1988 ሥራ ላይ እያለም የሰበር ሰሚ ችሎቱ በሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ መደበኛ ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች ወይም በሁለቱ የከተማ አስተዳደሮች እና የክልል በሆኑ ነዋሪዎች መካከል የሚነሱ የፍትሐብሔር ክርክሮች የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ስር የሚወድቁ ጉዳዮች ተብሎ ሲስተናገዱ ቆይተዋል፡፡ ይህ ማለት ግን አዲስ አበባ እና የድሬደዋ ከተማ አስተዳደር ክልል ስላልሆኑ በነዚህ የከተማ አስተዳደሮች እና በሕገ-መንግስቱ ክልል ተብሎ በሚታወቁት ነዋሪዎች መካከል የተነሳን የፍትሐ ብሔር ክርክርን የመዳኘት ሥልጣን የፌደራል ፍርድ ቤቶች ነው በማለት የሚደነግገው የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ቁጥር 5(1/ሸ) ከሕገ-መህግስቱ ጋር ስለሚጋጭ የሕገ-መንግስት ትርጉም እንዲሰጥበት ጥያቄ ማቅረብን፤ትርጉም እንዲሰጥ ጉዳዩ የተመራለት ተቋም ትርጉም እስኪሰጥ ድረስ የክርክር መዝገቡን ለጊዜው ዘግቶ ማቆየት አይችልም ማለት አይደለም፡፡ ነገር ግን በፌዴሬሽን ምክር ቤት የሕገ-መንግስት ትርጉም እንዲሰጥበት ከተመራው ጉዳይ ውጪ ባሉ ተመሳሳይ ጭብጥ የያዙ ጉዳዮች በሙሉ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በተላለፈ ትዕዛዝ መነሻነት ክርክሮችን ለጊዜው አግዶ የማቆየቱ ተገቢነት ሊመረመር ይገባል፡፡

በሕገ-መንግስት ትርጉም ላይ ምክር ቤቱ በሚሰጠው ውሳኔ በግልጽ ካልተመለከተ በስተቀር ተፈጻሚ የሚሆነው ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ እንደሆነ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤትን ሥልጣንና ተግባር ለመዘርዘር የወጣው አዋጅ ቁጥር 1261/2013 አንቀጽ 21/1 የሚደነግግ ሲሆን የሕገ-መንግስት ትርጉሙ በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ አስገዳጅነት የሚኖረው ወይም ሕገ-መንግስታዊ አይደለም የተባለው ድንጋጌ በሌሎች ጉዳይ ላይ ተፈፃሚ የማይሆነው ትርጉም ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ አልያም በውሳኔ ላይ ከተመለከተው ቀን አንስቶ እንጂ ትርጉም ያልተሰጠበትን ጊዜ ጨምሮ አይደለም፡፡ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በቀረበለት የሕገ-መንግስት ክርክር ጉዳይ በአመልካቹ ላይ ሊተካ የማይችል ጉዳት ይደርሳል ወይም ሁከትና ብጥብጥ ሊከሰት ይችላል ወይም ሌላ ከባድ አሳማኝ ምክንያት አለ ብሎ ሲያምን በአመልካች በሚቀርብ አቤቱታ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ በአፈ ጉባኤው የዕግድ ትዕዛዝ ሊሰጥ እንደሚችል የአዋጅ ቁጥር 19 ድንጋጌ ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩል በመታየት ላይ ያለ ጉዳይ በሕጉ የተመለከቱ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ(ሲሟሉ) ፍርድ ቤት ጉዳዩ በቀጠሮ እንዲቆይ፤ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በሥር ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ ወይም ተያያዥነት ያለው ጉዳይን

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማ አያገለግልም!

በሚመለከት ለጊዜው ታግዶ እንዲቆይ ትዕዛዝ ሊሰጥ እንደሚችል ከፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 197/2 እና 332 ድንጋጌዎች ያመለክታሉ፡፡ የኦሮሚያ ክልል መንግስት ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 216/2011 ቁጥር 29/1 ድንጋጌ መሠረት ፕሬዝዳንቱን እና ምክትል ፕሬዝዳንቱን ጨምሮ ቢያንስ አምስት የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች የተሰየሙበት ሰበር ችሎት የሚሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የክልሉን ፍርድ ቤቶች ሚያስገድደው በክልል ጉዳዮች ላይ የሚሰጠው የሕግ ትርጉምን የሚመለከት ሲሆን ነው፡፡

የቀረበለትን ጉዳይ አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ያለው መሆን አለመሆኑን አይቶ የመወሰን ስልጣን ያለው ጉዳዩን የያዘው ችሎት፣ ወይም ጉዳዩ በይግባኝ ወይም በሰበር የቀረበለት ችሎት እንጂ በተመሳሳይ ጉዳይ ተፈጻሚ እንዲሆን ትዕዛዝ ወይም በሰርኩላር መመሪያ ሊሰጥ የሚችልበት አግባብ አለመኖሩን፣ ችሎትም አስተዳደራዊ የሆነውን ሰርኩለር (መመሪያን) መሰረት በማድረግ የቀረበለትን የዳኝነት ጥያቄ አላስተናግድም በማለት የሚሰጥ ውሳኔ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 79(2 እና 3) እና የኦሮሚያ ክልል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 216/2011 ቁጥር 7/1 ሥር ከተመለከተው የዳኝነት ነፃነትን ጋር የሚጣረስ፣የዘገየ ፍትህ እንደተነፈገ ይቆጠራል ከሚለው ብሂል አንፃር ሲታይ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 37 ሥር የተመለከተውን ፍትሕ የማግኘት መብትን የሚገድብ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው በማለት የሰበር ሰሚ ችሎቱ በሰበር መዝገብ ቁጥር 247494 ላይ የሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10/2 ድንጋጌ መሠረት ከተሰጠበት ሰኔ 27 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ የሰበር ሰሚ ችሎቱን ጨምሮ በሀገሪቱ ውስጥ ባሉትን ሁሉም ፍርድ ቤቶች ላይ አስገዳጅነት አለው፡፡

በተያዘው ጉዳይ መደበኛ ነዋሪነታቸው በሀረሪ ክልል ሀረር ከተማ ኤረር ቀበሌ በሆኑ አመልካቾች እና በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሀረርጌ ዞን ባቢሌ ወረዳ ነዋሪ በሆኑት ተጠሪ መካከል የሚደረገውን የፌደራል ጉዳይ የሆነውን የውርስ ክርክር የምሥራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 80/4(ለ)፣በተሸሻለው የኦሮሚያ ክልል ሕገ-መንግስት አዋጅ ቁጥር 46/1994 አንቀጽ 64/3፣የኦሮሚያ ክልል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 216/2011 ቁጥር 30/4 ድንጋጌ መሠረት በውክልና አይቶ ውሳኔ መስጠት ሲገባው ከተያዘው ጉዳይ ጋር ምንም ግንኙነት በሌለው መዝገብ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት በቀጥር 3-228/838/15 ህዳር 30 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠውን ትዕዛዝ መሠረት አድርጎ መዝገቡን መዝጋቱ፣ ተጠሪ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት በቀጥር 3-228/838/15 ህዳር 30 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው መመሪያ መሠረት መዝገቡ ሊዘጋ ይገባል በማለት ያቀረቡትን መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ ክርክሩ እንዲቀጥል የሰጠውን ትዕዛዝ ከፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 208 ድንጋጌ ዓለማ ውጪ ጠቅሶ አስቀድሞ የሰጠውን ትዕዛዝ አንስቶ መዝገቡን

መዝጋቱ የክርክር አመራሩ ሥነ ሥርዓታዊ አለመሆኑን፤ የሰበር ሰሚ ችሎቱ በሰበር መዝገብ ቁጥር 37303(በቅጽ 8 እንደታተመው)፤ በሰበር መዝገብ ቁጥር 95649(በቅጽ 16 እንደታተመው) የሰጠውን አስገዳጅ ውሳኔ የሚቃረን፤ የሰበር ሰሚ ችሎቱ በተመሳሳይ ጉዳይ በሰበር መዝገብ ቁጥር 247494 የሰጠውን አስገዳጅ ውሳኔን የሚጣረስ፤ከላይ በስፋት በውሳኔ ውስጥ የተመለከቱን የሕገ-መንግስቱን አንቀጽ 37፤79(2 እና 3) ፤ እንዲሁም 80/3(ለ) እና (4)፤የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤትን ሥልጣንና ተግባር ለመዘርዘር የወጣው አዋጅ ቁጥር 1261/2013 ቁጥር 21/1 እና ቁጥር 19 ድንጋጌ፤የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ቁጥር 5(1/ሸ)ን፤ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉን ቁጥር 197/2፤208 እና 332 ድናጋጌዎችን፤ የተሸሻለው የኦሮሚያ ክልል ሕገ-መንግስት አዋጅ ቁጥር 46/1994 አንቀጽ 63/2 እና(3)፤እንዲሁም 64/3፤የኦሮሚያ ክልል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 216/2011 ቁጥር 7 እና 29 እና ሌሎችን ድንጋጌዎችን ያላገናዘበ በመሆኑ ከአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሀ፤(ለ)፤(ሸ) እና10(1/ሠ)አንጻር ሲታይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ሆኖ ስለተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምሥራቅ ቋሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 434944 ላይ ታህሳስ 12 ቀን 2016 ዓ.ም በዋለው ችሎት የምሥራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጥቅምት 12 ቀን 2016 ዓ.ም በዋለው ችሎት በመዝገብ ቁጥር 103512 የሰጠውን ትዕዛዝ በማጽናት የሰጠው ውሳኔ እና ትዕዛዝ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የምሥራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍርድ የዘጋውን የመዝገብ ቁጥር 103512 በማንቀሳቀስ ግራ ቀኙን አከራክሮ ተገቢውን ሕጋዊ ውሳኔ እንዲሰጥ በሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/2 መሰረት ጉዳዩን መልሰንላታል፡፡ ይጻፍ፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ውሳኔ አግኝቶ ስለተዘጋ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 265504

ታህሳስ 21 ቀን 2017ዓ/ም

**ዳኞች ፡-   ገበየሁ ፈለቀ**

**ደረጀ አያና**

**ደጀኔ አያንሳ**

**ኑረዲን ከድር**

**ብርሃኑ መንግሥቱ**

**አመልካች፡-  አማኑኤል ያዘዉ ተፈሪ - አልቀረቡም**

**ተጠሪ ፡-  የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ - ዐቃቤ ሕግ - አልቀረቡም**

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የወንጀል ቅጣት ሲወሰን የፍርድ ቤቶች ፍቅድ ሥልጣን አተገባበር የሚመለከት ነው፡፡ክርክሩ የተጀመረው በኦሮሚያ ክልል በሸገር ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ በአመልካች እና በስር 2ኛ ተከሳሽ ታምራት ቶማስ ላይ በመሠረተዉ የወንጀል ክስ መነሻ ሲሆን በአመልካች የቀረበበት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካችና የስር 2ኛ ተከሳሽ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1/ሀ) እና በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 168/2 ስር የተደነገገዉን በመተላለፍ አመልካች በሚያሽከረክረዉ ንብረትነቱ የራሱ በሆነና በሰሌዳ ቁጥሩ 3-B68600አአ በሚታወቅ ተሽከርካሪ አገር ዉስጥ እንዳይገቡ የተከለከሉ መሆኑን እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባዉ ግምቱ ብር 28,500.00 የሆነ 149 ጥንድ አሮጌ ኮንትሮባንድ ጫማዎችን፤ እንዲሁም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ንብረትነቱ የስር 2ኛ ተከሳሽ የሆነ ግመታቸዉ ብር 19,000.00 የሆነ አሮጌ ልባሽ ልብሶችን በቀን 27/04/2016ዓ/ም ከቀኑ በግምት 10:00 ሰዓት ላይ ከሐዋሳ ከተማ ወደ አዲስ አበባ ከተማ ጭኖ ሲያጓጉዝ በሸገር ከተማ ገላን ክፍለ ከተማ ላይ በመያዛቸዉ በፈጸሙት የኮንትሮባንድ ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነዉ፡፡

ፍርድ ቤቱም ለአመልካችና ለስር ተከሳሽ የክስ ማመልከቻዉ እንዲደርሳቸዉ አድርጎ አንብቦላቸዉ አመልካች በክሱ የተገለጹትን ዕቃዎች በተሽከርካሪዉ ጭኖ ሲያጓጉዝ እንደነበር ሳይክድ አሮጌ ጥንድ ጫማዎች ከሐዋሳ ከተማ ከሕዝብ መገበያያ ገበያ ባዛር ላይ የገዛሁት ስለሆነ ወንጀሉን አልፈጸምኩም፤ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ክዶ በመከራከሩ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች ተሰምተዋል፡፡የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች በክሱ የተጠቀሱትን የኮንትሮባንድ እቃዎች አመልካች በተሽከርካሪዉ ጭኖ ሲያጓጉዝ ይዘነዋል በማለት መስክረዋል፡፡ፍርድ ቤቱም ይህንን ተከትሎ አመልካችና የስር 2ኛ ተከሳሽ ክሱን እንዲከላከል ወስኗል፡፡አመልካች አቅርቦ ያሰማቸዉ ምስክሮች አመልካች ጥንድ ጫማዎችን ከሐዋሳ ከተማ ከባዛር ገበያ ላይ መግዛቱን መስክረዋል፡፡ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ማስረጃዎች መርምሮና መዝኖ አመልካች ኮንትሮባንድ ወንጀል እንደፈጸመ በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ የተረጋገጠባቸዉን በማስተባበል አልተከላከሉም በማለት በወነጀል ሕግ አንቀጽ 32(1/ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 168/2 ስር ጥፋተኛ ናቸዉ በማለት ፍርድ ሰጥቷል፡፡ይህንን ተከትሎ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሠረት ለወንጀል ቅጣቱ ደረጃ እና እርከን በማዉጣት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ በመመደብ መነሻ ቅጣቱን ሦስት ዓመት በመያዝ በእርከን 14 ላይ በማሳረፍ የገንዘብ መቀጮዉንም በተመመሳሳይ ደረጃ በማዉጣት የአመልካችን ሦስት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች በመያዝ፤የስር 2ኛ ተከሳሽን ሁለት የቅጣት ማቅላያ ምክንያቶችን በመያዝ እንደቅደምተከተላቸዉ የእስራት ቅጣቱን ወደ እርከን 11 እና 12 ዝቅ በማድረግ እንደቅደምተከተላቸዉ እያንዳንዳቸዉ በ2 (ሁለት) ዓመት ጽኑ እስራትና በብር 10,000.00(አስር ሺህ ብር) የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ወስኗል፡፡አመልካች በዉሳኔዉ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ቢሆንም ተሰርዞበታል፡፡

አመልካች በቀን 26/09/2016 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉ ከላይ በተመለከተዉ መሠረት በተሰጠ የጥፋተኝነትና የቅጣት ዉሳኔ ላይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን ይዘቱም በአጭሩ ጫማዎቹን ለሕዝብ ግልጽ ከሆነ ገበያ ቦታ ላይ ገዝቼ ለቤተሰቦቼና ለጎረቤት ልጆች ለመለገስ የገዛሁት እንደሆነና ከዉጭ አገር እንዳላስገባሁ በመከላከያ ማስረጃዎቼ አስረድቼ እያለሁ ጥፈተኛ መባሌ ሕጉን ያልተከተለና የማስረጃ ምዘና ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡ባቀረብኩት ሦስት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች መሠረት መቀጣት የሚገባኝ በእርከን 11 ስር በአንድ ዓመት ከስምንት ወር መሆን ሲገባ ሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ከተያዙለት ከስር 2ኛ ተከሳሽ ጋር እኩል በ2(ሁለት) ዓመት ጽኑ እስራት እንድቀጣ መወሰኑ ስህተት ነዉ፡፡እንዲሁም ለአባይ ግድብ 3 ጊዜ ቦንድ መግዛቴ፣ሁለት ጊዜ ደም በመለገስ በጎ አድራጎት ሥራ መፈጸሜ እና ለአረንጓዴ አሻራ ልማት የሚሰማሩ ሰዎችን በራሴ መኪና በማመላለስ ላበረከትኩት አስተዋጽኦ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 86 መሠረት የቅጣት ማቅለያ ተደርጎ እንዲያዝልኝ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

የጠየቅሁት ሳይያዝልኝ መታለፉ ስህተት ስለሆነ እንደልዩ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ተይዞ ተሻሽሎ ይወሰንልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ችሎቱ የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ከስር ፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ፍርድና ከቅጣት ዉሳኔ ጋር አገናዝቦ መርምሮ ከቅጣት ዉሳኔ አሰጣጥ አኳያ አመልካች የስር 2ኛ ተከሳሽ ካቀረበዉ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ጋር ሲነጻጸር ሦስት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን አቅርቦ ሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ካቀረበዉ 2ኛ ተከሳሽ ጋር እኩል ቅጣት እንዲቀጣ የተወሰነበትን አግባብ ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ አዝዟል፡፡ተጠሪ በቀን 12/03/2017 ዓ/ም በተጻፈ መልሱ ከቅጣት ዉሳኔ አንጻር የተፈጸመ ስህተት ካለ ቢታረም የሚል መልስ ሰጥቷል፡፡

ከላይ አጠር ባለ መልኩ የተገለጸዉ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ውሳኔዎች እንዲሁም የግራ ቀኙን ክርክር የሚመለከት ሲሆን እኛም አስቀድሞ የተያዘዉን ጭብጥ ከግምት በማስገባት አመልካች ሦስት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን አቅርቦ ሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን ካቀረበዉ ከስር 2ኛ ተከሳሽ ጋር እኩል እንዲቀጣ በመወሰኑ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የሕግ ስህተት መፈጸም አለመፈጸሙን እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

በአገራችን በተዘረጋዉ የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሥርዓት መሠረት ሕገ-ወጥነቱና አስቀጪነቱ በሕግ የተደነገገዉን በማድረግ የሚፈጸም የወንጀል ድርጊትም ሆነ አል ድርጊት ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮችን በአንድነት በሚያሟላ አኳኋን ስለመፈጸሙ በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ በፍርድ ቤት የተረጋገጠበት ወንጀል ፈጻሚ በወንጀል ሕጉ ወይም አግባብነት ባለዉ ሌላ ሕግ የተደነገገዉን ተገቢ ቅጣት መቀጣት ይገባዋል፡፡ ፍርድ ቤቶች በዚህ አግባብ የወንጀል ቅጣት ሲወስኑ የወንጀል ሕጉን ዓላማዎች እና ግቦች ባገናዘበ አኳኋን ዉጤታማና ተገማችነት ያለዉን ቅጣት የመወሰን ኃላፊነት አለባቸዉ፡፡ ፍርድ ቤቶች ይህንን ለማሳካት ከግምት ማስገባት ከሚገባቸዉ ነገሮች መካከል አንዱ በተቀራራቢና ተመሳሳይ የወንጀል ጉዳዮች መካከል ተቀራራቢነት ያለዉን ቅጣት መወሰን ሲሆን ሌላዉ ደግሞ እንደ ወንጀሉ ከብደትና አደገኛነት የቅጣትን ተመጣጣኝነት ማረጋገጥ ነዉ፡፡ ይህ በሚገባ ይሳካ ዘንድ ሕግ አዉጪዉ በወንጀል ሕጉ ቅጣት ሲወሰን ከግምት ሊገቡ የሚገባቸዉን ጠቅላላ መርሆዎች፣ሁኔታዎችና ሥርዓቶች ከመደንገጉም ባለፈ በሕጉ አንቀጽ 88/4 የቅጣት አወሳሰንን ትክክለኛነትና ወጥነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል የቅጣት አወሳሰን መመሪያ እንዲያወጣ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሥልጣን ሰጥቶታል፡፡ በዚህ መሰረት ተሻሽሎ በወጣዉ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 የወንጀል ቅጣትና የጥንቃቄ እርምጃዎች የሚወሰንበት አግባብ ተደንግጓል፡፡እንዲሁም የወንጀል ቅጣት ሲወሰን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 88 ላይ ፣ በወንጀል ሕጉ ጠቅላላ ክፍል ድንጋጌዎች ላይ እና ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በሚደነግጉት የልዩ ክፍሉ ድንጋጌዎች ላይ የተደነገገዉን መሠረት ማድረግ ይገባል፡፡ይኸዉም የወንጀል አድራጊውን ግላዊ የአደገኛነት መጠን፣ ያለፈ የህይወት ታሪኩን፣ ወንጀል ለማድረግ ያነሣሡትን ምክንያቶችና የአሣቡን ዓላማ፣ የግል ኑሮውን ሁኔታ፣

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

የትምህርቱን ደረጃ፣ እንዲሁም የወንጀሉን ከባድነትና የአፈፃፀሙን ሁኔታዎች በማመዛዘን የወንጀል ሕግ ልዩ ክፍል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነዉ ፍርድ ቤቱ በጣም ቀላል ከሆነው ቅጣት አንስቶ እስከ ከባዱ ድረስ ያለውን በጥንቃቄ በመመርመር ለእያንዳንዱ ጉዳይ ተገቢ የሆነውን ቅጣት መወሰን እንደሚገባ የሚያስገነዝብ ነዉ፡፡

በተጨማሪም ፍርድ ቤቶች ወይም ዳኞች የወንጀል ቅጣት ሲወስኑ በሕግ የተሰጣቸዉን ዳኝነታዊ ፍቃደ ሥልጣን (judicial discretion) በአግባቡ መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡ ፍርድ ቤቶች ወይም ዳኞች ዳኝነታዊ ፍቃደ ሥልጣን በአግባቡ የማይጠቀሙ ከሆነ የዘፈቀደ አሠራር እንዲፈጠር በማድረግ ተመሳሳይ ጉዳይ ላይ የተለያየ እና ተገማች ያልሆነ ቅጣት እንዲወሰን በር በመክፈት በዜጎች መካከል ልዩነት እንዲፈጠር ከማድረግም በተጨማሪ የዳኝነት ነጻነትና የዳኝነት ሥራ ገለልተኝነት መርሆዎች እንዲጣሱ ስለሚያደርግ በፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ላይ እንዲህ አይነት ጉድለት ሲኖር እንደመሰረታዊ የሕግ ስህተት ተቆጥሮ ሊታረም የሚገባ ስህተት ይሆናል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች ጥፋተኛ የተባለዉ ወደ አገር ዉስጥ እንዳይገቡ ገደብ የተደረገባቸዉና በሕገ-ወጥ መንገድ የተገኙ እንደሆኑ እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባዉ ጠቅላላ ግምታቸዉ ብር 28,500.00 የሆኑ 149 ጥንድ አሮጌ ጫማዎችን ሲያጓጉዝ በመያዙ በአዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 168 ስር የተደነገገዉን የኮንትሮባንድ ወንጀል በመፈጸሙ እንደሆነ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ያሳያል፡፡በሌላ በኩል የስር 2ኛ ተከሳሽ በተመሳሳይ ድንጋጌ ጥፋተኛ የተባለዉ ወደ አገር ዉስጥ እንዳይገቡ ገደብ የተደረገባቸዉና በሕገ-ወጥ መንገድ የተገኙ እንደሆኑ እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባዉ ጠቅላላ ግምታቸዉ ብር 19,000.00 የሆኑ አሮጌ ልባሽ ጨርቆችን(ልብሶችን) በአመልካች ተሽከርካሪ ላይ አስጭኖ ሲያጓጉዝ በመያዙ ነዉ፡፡ከላይ እንደተገለጸዉ በአመልካች ላይም ሆነ በስር 2ኛ ተከሳሽ ላይ ቅጣት ሲወሰን የእያንዳንዳቸዉ ግላዊ የአደገኛነት መጠን፣… ወንጀል ለማድረግ ያነሣሣቸዉን ምክንያቶችና የአሣባቸዉን ዓላማ፣ የግል ኑሮአቸውን ሁኔታ፣ የትምህርታቸዉን ደረጃ፣ እንዲሁም የወንጀሉን ከባድነትና የአፈፃፀሙን ሁኔታዎች ማመዛዘን ይገባል፡፡ ከእነዚህ ሁኔታዎች አንጻር ሲታይ አመልካች ሲያጓጉዝ የነበረዉ እቃ ግምት 2ኛ ተከሳሽ አስጭኖ ሲያጓጉዝ ከነበረዉ እቃ ግምት የሚበልጥ ሲሆን እቃዎቹ ሲጓጓዙ የነበረዉ በአመልካች ተሽከርካሪ በመሆኑ የአመልካች ግላዊ አደገኛነት እንዲሁም አመልካች ሲያጓጉዝ የነበረዉ ዕቃ ዋጋ በንጽጽር ከፍ ያለ ከመሆኑ አንጻር ሲታይ የወንጀል ክብደት ከስር 2ኛ ተከሳሽ ከፍ ያለ መሆኑ በግልጽ የሚታይ ነዉ፡፡

ከላይ የተመለከተናቸዉን ሁኔታዎች ከግምት በማስገባት የስር ፍርድ ቤት ቅጣት መወሰን አለመወሰኑን ስናይ አመልካች ያቀረባቸዉ ሦስት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ሲያዙለት ቅጣቱ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ እርከን 11 ላይ የሚያርፍ ሲሆን ይህም *ከአንድ ዓመት ከስምንት ወር እስከ ሁለት ዓመት ከሁለት ወር* የሚያስቀጣ ነዉ፡፡በሌላ በኩል የስር 2ኛ ተከሳሽ ያቀረበዉ ሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ሲያዙለት ቅጣቱ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ እርከን 12 ላይ የሚያርፍ ሲሆን ይህም *ከሁለት ዓመት እስከ ሁለት*

**ማስታወሻ፡** - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ዓመት ከስድስት ወር የሚያስቀጣ ነዉ፡፡በሁለቱም እርከን ላይ ያለዉ የእስራት ቅጣት ዳኞች የሁለት ዓመት የእስራት ቅጣት እንዲወስኑ ፍቃደ ሥልጣን የሚሠጥ ነዉ፡፡ስለሆነም አመልካች ከስር 2ኛ ተከሳሽ የተሻለ ቀለል በሚል እርከን 11 ላይ ሊቀጡ የሚገባ በመሆኑ ብቻ በማንኛዉም ጊዜና ሁኔታ ከስር 2ኛ ተከሳሽ ያነሰ ቅጣት መቀጣት አለባቸዉ የሚባልበት የሕግ መሠረት የለም፡፡አመልካች በእርከን 11 ላይ ከስር 2ኛ ተከሳሽ ያነሰ ቅጣት ሊቀጡ የሚገባዉ ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 88/2 አንጻር ሲታይ ዝቅተኛ ቅጣት ሊያስወስን የሚችል የግሉ የሆነ ምክንያትና ሁኔታ ሲኖር ነዉ፡፡ነገር ግን ከዚህ በላይ እንደተገለጸዉ የአመልካች ግላዊ የአደገኛነት መጠን እና በአመልካች የተፈጸመዉ ወንጀል ክብደት ሲታይ አመልካች በእርከን 11 ስር ከሁለት ዓመት ያነሰ ወይም የስር 2ኛ ተከሳሽ ከተቀጣዉ የእስራት ቅጣት ያነሰ ቅጣት እንዲቀጣ የሚያደርግ አይደለም፡፡

ሲጠቃለል የስር ፍርድ ቤቶች በአመልካች ላይ ባስተላለፉት የቅጣት ዉሳኔ ሕግን አልተከተሉም ወይም ፍቃደ ሥልጣናቸዉን በአግባቡ ተግባራዊ አላደረጉም የሚያስብል ምክንያት ባለመገኘቱ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2/4 እና 10(1/ሠ) መሰረት በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ባለመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የሸገር ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 77184 ላይ በቀን 20/07/2016ዓ.ም የሰጠዉ የጥፋተኝነት ፍርድ እና የቅጣት ዉሳኔ እንዲሁም የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 35700 ላይ በቀን 17/08/2016ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 መሰረት ጸንተዋል፡፡

## ትዕዛዝ

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ እንዲያዉቀዉ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ለግራ ቀኙም ግልባጬ ይሰጣቸዉ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
## የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 270511

ታህሳስ 25 ቀን 2017 ዓ/ም

ዳኞች ፡- ገበየሁ ፈለቀ

ደረጀ አያና

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

ብርሃኑ መንግሥቱ

**አመልካች - ምኞት ካሣ ብሩ**

**ተጠሪ - የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ፍትህ ቢሮ - ዐቃቤ ሕግ**

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የአመልካች የዋስትና መብት ይከበርልኝ ጥያቄ ዉድቅ ተደርጎ በመወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ለማሳረም የቀረበ የሰበር አቤቱታ የሚመለከት ነዉ፡፡ ክርክሩ የተጀመረዉ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጎፋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪ በአመልካች ላይ በመሰረተዉ ክስ 1 - አመልካች የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ በወጣውን አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 32/2 ስር የተደነገገዉን በመተላለፍ በሳውላ ከተማ አስተደደር ገቢዎች ጽ/ቤት የዕለት ገቢ ሰብሳቢ ሆና በምትሰራበት ጊዜ ከቀን 01/02/2013 እስከ 30/4/2016 ዓ.ም ድረስ ገቢ ለመሰብሰብ በሞዴል 22 ከሳውላ ከተማ ፋይናንስ ጽ/ቤት

ንብረት ክፍል ወጪ ያደረገችውን የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት መደበኛ ጥራዝ ካርኒ ብዛት 368 ከሆነው ውስጥ በ20 ካርኒ ቅጠል እያንዳንዱ 3 ኮፒ በያዘው ተመሳሳይ ን/ቁ ባላቸው ገቢ ስትሰበስብ የካርኒው 1ኛ ኮፒ ለግብር ከፋይ 2ኛ ኮፒ ለግብር ከፋይ ግል ማህደርና 3ኛ ኮፒ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት የሚቀርብና ኦዲት የሚደረግ ሲሆን በሶስቱም ካርኒዎች ተመሳሳይ የግብር ከፋይ ስም የከፈለው ገንዘብ መጠንና ገንዘቡ የተከፈለበት ምክንያት የክፍያ ርዕስ ኮድ መፃፍ ሲገባት በ3ኛ ኮፒ ኦዲት በሚደረገው ካርኒ የግብር ከፋይ ስም የከፈለው ገንዘብ መጠን በማሳነስ እና የተከፈለበት ምክንያት በመቀየር በ20 ቅጠል ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 31/2 ስር የተደነገገዉን በመተላለፍ በክስ 1 በተገለፀው ጊዜና ስፍራ በሞዴል 22 ወጪ አድርጋ ከተቀበለችው 368 ጥራዝ ካርኒ በማታለል ለግል ከተጠቀመች ውስጥ 20 ቅጠል ወጪና ገቢ የሰበሰበችው ገንዘብ ብር 26,919,915.00 ሲሆን በሞዴል 64 የተጠቃለለ ጠቅላላ ወጪ ብር 26,807,301.00 ልዩነት በጉድለት የታየው ብር 112,614.00 ለራስዋ ለማግኘት ከባድ የእምነት ማጉደል ወንጀል ፈፅማለች የሚል ነው፡፡

አመልካችም 1ኛ ክስን በተመለከተ ሙሉ በሙሉ በማመን የማታለል ወንጀል ፈፅሜአለው ጥፋተኛ ነኝ ብላ አስመዝግባ 2ተኛውን ክስ በተመለከተ ግን ክዳ ተከራክራለች፡፡በዚህም ፍርድ ቤቱ አመልካች ከተጠቀመችው ገንዘብ መጠን አንፃር ክስ የቀረበበትን ድንጋጌ በመቀየር በክስ 1 በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 32/1 ስር በክስ 2 ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 31/1 ስር እንድትከላከል ብይን ሰጥቷል፡፡ይህንን ተከትሎ አመልካች የዋስትና መብቷ እንዲጠበቅላት ጠይቃ ተጠሪ በሰጠዉ አስተያየት - አመልካች ትከላከል የተባለችባቸዉ ሁለቱ ድንጋጌዎች ቅጣት ሲደመር ከ10 ዓመት በላይ በመሆኑ ይህ ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/2 ላይ ዋስትና ስለሚከለክል የዋስትና መብቷ ሊጠበቅ አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡ፍርድ ቤቱም አመልካች በክስ 1 እንድትከላከል የተበየነዉ ቅጣት ጣሪያ ከ3 ዓመት እስከ 10 ዓምት ሲሆን በክስ 2 ላይ የቅጣት ጣሪያው ከ3 ዓመት እስከ 7 ዓመት በመሆኑ የሁለቱ ድንጋጌዎች ቅጣት ጣሪያ ሲደመር ከ10 ዓመት በላይ ስለሆነ አመልካች የዋስትና መብቴ ይጠበቅልኝ በማለት ያቀረበችዉ ጥያቄ ተቀባይነት የለዉም በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበች ሲሆን ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 004723 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 07/12/2016 ዓ.ም በሰጠዉ ፍርድ የስር ፍርድ ቤት ብይን ጉድለት የለበትም በማለት አጽንቷል፡፡አመልካች በመቀጠል የሰበር አቤቱታዋን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ብታቀርብም ችሎቱ በመ/ቁጥር 004815 ላይ በቀን 22/12/2016 ዓ.ም በሰጠዉ ትእዛዝ የሕግ ስህተት አልተፈጸመበትም በማለት ሠርዞባታል፡፡

አመልካች ለዚህ ችሎት በቀን 06/01/2017 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ በጠበቃዋ አማካኝነት ያቀረበችዉ ከላይ በተጠቀሰው መሰረት የተሰጠው ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ሲሆን ይዘቱም በአጭሩ - አመልካች በእርግዝና ምክንያት የጤና መታወክ ስለገጠመኝ የሐክም የቅርብ ክትትል

እንደሚያስፈልገኝ በመረጋገጡ ለአመልካችም ሆነ ለምወልደዉ ሕጻን ድህንነት በዋስትና ተለቅቄ እንዲከራከር ያቀረብኩትን ጥያቄ የሥር ፍርድ ቤቶች አለመቀበላቸዉ ኢትዮጵያ የተቀበለችዉን ዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብቶች ሰነዶች የሴቶችና የሕጻናትን መብቶች ለማስከበር የወጣዉን ስምምነት አንቀጽ 12/2፣18/2 እና 24(2/መ)ን እና በአፍሪካ የሕጻናት መብቶች ቻርተር አንቀጽ 20(2/ሀ) ስር የተደነገገዉን የሚቃረን ነዉ፡፡በአመልካች ተፈጸመ የተባለዉ የወንጀል ድርጊት ለወደፊት ጥፋተኛ ስትሆን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 61/1 መሰረት በአንድ አንቀጽ ስር የሚጠቃለል ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች ለወደፊት የማትቀጣበትን ድንጋጌ ለዋስትና ክልከላ መሠረት በማድረግ የዋስትና መብቷ ሊጠበቅ አይገባም በማለት የሰጡት ዉሳኔ በሰ/መ/ቁጥር 134549 ላይ የተሰጠዉን የሕግ ትርጉም የሚቃረን ነዉ፡፡እንዲሁም አመልካች እንድከላከል ብይን የተሰጠው ከ3 ዓመት በላይ እና ከ10 ዓመት በታች ጽኑ እሥራት በሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች በመሆኑ የቅጣቱ ድምር ከ10 ዓመት በላይ መሆኑ የዋስትና መብት እንደማያስከለክል እንደገና በተሻሻለው የፀረ ሙስና ልዩ ሥነ ሥርዓትና ማስረጃ አዋጅ ቁጥር 882/007 አንቀጽ 3(1) ተደንግጎ እያለ ይህንን በሚቃረን መልኩ የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካችን የዋስትና መብት በመንፈግ የሰጡት ዉሳኔ ስለሆነ ታርሞ የአመልካች የዋስትና መብት ተጠብቆ ይወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

ችሎቱ የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች ይከላከሉ የተባሉባቸው አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 32/1 እና 31/1 ሁለቱ ድንጋጌዎች ቅጣት ጣሪያ ድምር ከ10 አመት በላይ ሊያስቀጣ የሚችል ነው በማለት የተሻሻለውን የጸረ ሙስና ልዩ ሥነ ሥርአትና ማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 ስር በሁለተኛዉ ዐረፍተ ነገር ላይ የተመለከተውን መሰረት በማድረግ የአመልካችን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት በአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 ላይ ከአራት ዓመት በላይ እና ከ10 ዓመት በታች የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ሲኖሩ እየተደመሩ ከ10 ዓመት በላይ የሚያስቀጣ ከሆነ ዋስትናን ይከለክላል የሚለው የተደራራቢ ወንጀሎች መነሻ ቅጣትን የሚመለከት ነው? ወይስ ጣሪያ? የሚለው ሰበር ችሎቱ ከዚህ በፊት በሰ/መ/ቁ 182050 (በቅጽ 24 የታተመ) ከተሰጠው የህግ ትርጉም እና ከኢፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት በአንቀጽ 19 (6) እና ከአዋጁ መሰረታዊ ዓላማ አንጻር የድንጋጌው ሁለተኛ ዐረፍተ ነገር በምን አግባብ ተግባራዊ ሊሆን ይገባል የሚለውን ጭምር ለመመርምር ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት አዝዟል፡፡

ተጠሪ በቀን 04/04/2017 ዓ.ም በተጻፈ መልሱ - ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 182050 (ቅጽ 24) ላይ በሰጠዉ የሕግ ትርጉም በተሻሻለዉ አዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 ሁለተኛ ዐረፍተ ነገር ላይ ከአራት አመት በላይ በሚል የተደነገገዉን በመተርጎም እንደ መነሻ ቅጣት በመዉስድ የቅጣት መነሻቸዉ አራት ዓመት ጽኑ እስራት የሚያስቀጡ ወንጀሎችን የሚመለከት አድርጎ በመዉሰድ ዋስትናን መከልከሉ አግባብነት የሌለዉ ሆኖ አግኝተነዋል በማለት ትርጉም የሰጠ ሲሆን አሁን ላይ በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች እንድትከላከል ብይን የተሰጠበት ሲሆን ይህ ችሎት ከዚህ ቀደም የተሰጡ የሰበር ዉሳኔዎችን እና የሙስና

ወንጀሎች አዋጆችን እንዲሁም አለም አቀፍ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ ሕጋዊዉን ትርጉም ይስጥልን በማለት ተከራክሯል፡፡

ከላይ አጠር ባለ መልኩ የተገለጸዉ በክልሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች እንዲሁም የግራ ቀኙን ክርክር የሚመለከት ሲሆን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም ከፍ ሲል ከተጠቀሰዉ ጭብጥ አንፃር ጉዳዩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

እንደተመረመረዉም በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 17/2 ስር ማንኛዉም ሰዉ በሕግ ከተደነገገዉ ሥርዓት ዉጭ ሊያዝ፣ክስ ሳይቀርብበት ወይም ሳይፈረድበት ሊታሰር እንደማይችል በመደንገግ ለነጻነት መብት ጥበቃ ተደርጓል፡፡ይህ መብት የሀገራችን የሕግ አካል በሆነዉ በተባበሩት መንግሥታት የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን አንቀጽ 9/1 ላይ በግልጽ እዉቅና የተሰጠዉ መብት ነዉ፡፡በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 19/6 ስር የተያዙ ሰዎች በሕግ በተደነገገ ልዩ ሁኔታዎች ፍርድ ቤት የዋስትና መብት ጥያቄዎችን ላይቀበል የሚችልበት ወይም በገደብ መብታቸዉን የሚያስጠብቅበት ሁኔታ ሊኖር የሚችል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በመርህ ደረጃ በዋስ የመፈታት መብት እንዳላቸዉ ተደንግጓል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች የተከሰሰችዉ በሁለት ተደራራቢክሶች ሆኖ የመጀመሪያዉን ክስ በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 32/2 ስር የተደነገገዉን በመተላለፍ ከባድ አታላይነት ወንጀል ፈጽማለች በሚል ሲሆን 2ኛዉን ክስ ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 31/1 ስር የተደነገገዉን በመተላለፍ ከባድ የእምነት ማጉደል ወንጀል ፈጽማለች በሚል ነዉ፡፡ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠዉ ብይን አመልካች የተከሰሰችበትን ድንጋጌ ወደ አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 32/1 እና 31/1 በመለወጥ አመልካች ሁለቱንም ክሶች እንድትከላከል ብይን ሰጥቷል፡፡ይህንን ተከትሎ አመልካች የዋስትና መብቷ እንዲጠበቅላት ያቀረበችዉ ጥያቄ በየደረጃዉ ባሉ ፍርድ ቤቶች በተሰጠ ዉሳኔ ተቀባይነት ያጣዉ እንደገና በተሻሻለዉ የፀረ ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 4/1 በሁለተኛ ዐረፍተ ነገር ላይ በተደነገገዉ እና በሰ/መ/ቁጥር 182050 (ቅጽ 24) ላይ በተሰጠዉ የሕግ ትርጉም መሠረት አመልካች ትከላከል የተባለችባቸዉ ድንጋጌዎች ላይ የተመለከተዉ ቅጣት በድምሩ ከአስር ዓመት በላይ የሚያስቀጣ በመሆኑ የዋስትና መብት እንዲጠበቅላት ያቀረበችዉ ጥያቄ ተቀባይነት የለዉም በማለት ነዉ፡፡

አመልካች ትከላከል የተባለችበት የአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 31/1 ከሦስት ዓመት እስከ ሰባት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ሲሆን ሁለተኛዉ የአዋጁ አንቀጽ 32/1 ደግሞ ከሦስት ዓመት አስከ አስር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ነዉ፡፡እነዚህ ሁለቱም ድንጋጌዎች መነሻ ቅጣታቸዉ ከአራት ዓመት በታች የሆነ ጽኑ እስራት ነዉ፡፡

በሌላ በኩል አዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 4/1 ስር የተደነገገዉን ሁለተኛዉን ዐረፍተ ነገር መመልከት አስፈላጊ ይሆናል፡፡ይዘቱም ፡-

*"…ከአራት ዓመት በላይ እና ከአስር ዓመት በታች የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ሲኖሩም እየተደመሩ ከአስር ዓመት በላይ የሚያስቀጣ ከሆነ ዋስትና ይከለከላል።"* የሚል ነዉ።

ከላይ ይዘቱ የተጠቀሰዉን ድንጋጌ አተገባበር በተመለከተ ይህ ሰበር ችሎት የሰ/መ/ቁጥር 182050 እና 183488 ላይ አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቷል።በእነዚህ መዛግብት ላይ የተሰጠዉም ትርጉም በአጭሩ፡-

*"…ከአራት ዓመት በላይ እና ከ10 ዓመት በታች የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች በማለት የተገለጸው ሀሳብ ከአራት ዓመት በላይ በጽኑ እሥራት ሊያስቀጡ የሚችሉ ወንጀሎችን የሚመለከት እንጂ የቅጣት መነሻቸው አራት ዓመት የሆነ በጽኑ እሥራት የሚያስቀጡ ወንጀሎችን የሚመለከት እንዳልሆነ ከድንጋጌው አቀራረጽ እና ይዘት መገንዘብ ይቻላል።ተደራራቢ ወንጀሎች ተፈጽመው በተገኙ ጊዜ በሚል የተገለጸው የዐረፍተ ነገሩ ሁለተኛ ሀሳብ ደግሞ መነሻ ቅጣትን የሚመለከት ሳይሆን በቀላል እሥራት የሚያስቀጡ ወንጀሎች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 106/1 መሠረት ከ10 ቀን እስከ ሶስት ዓመት የሚያስቀጡ ስለሆኑ እነዚህ በቀላል አስራት የሚያስቀጡ የሙስና ወንጀሎች የፈለገውን ያህል ተደራርበው ቢገኙ ሌላ ሕጋዊ ምክንያት እስካልቀረበ ጊዜ ድረስ ተደራራቢ ወንጀሎች ናቸው በሚል ምክንያት የተከሰሰውን ሰዉ የዋስትና መብት መከልከል የማይቻል መሆኑን የሚያስገነዝብ ነዉ። ሆኖም ከአራት ዓመት በላይ እና ከ10 ዓመት በታች በሆነ ጽኑ እሥራት የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ሲኖሩ እና እየተደመሩ ከ10 ዓመት በላይ የሚያስቀጣ ከሆነ ግን የተከሰሰውን ሰው የዋስትና መብት የሚከለከል መሆኑን የሚያሳይ ነው።…" የሚል ትርጉም የተሰጠበት ነዉ።*

*በሌላ በኩል በዚህ ትርጉም ላይ የተገለጸዉ ሌላዉ ነገር ተከሳሹ በተከሰሰባቸዉ ተደራራቢ ክሶች ላይ የተጠቀሰዉ ወይም ይከላከል የተባለባቸዉ ድንጋጌዎች የቀላል እስራትና የጽኑ አስራት አማራጭ ቅጣቶችን የያዙ ከሆኑ ደግሞ የዋስትና መብት ለመጠበቅ ዓላማ የቀላል እሥራት አማራጭ ተወስዶ የዋስትና መብት አጠባበቅ ላይ ዉሳኔ ሊሰጥ እንደሚገባ ትርጉም የተሰጠበት ነዉ።*

በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10/2 እና 26 ጣምራ ንባብ መሠረት ከሠባት ያላነሱ የተሰየሙበት የሰበር ችሎት በሌላ ትርጉም እስሚለዉጥ ድረስ ከአምስት ያላነሱ ዳኞች የተሰየሙበት የሰበር ችሎት የሚሰጠዉ የሕግ ትርጉም ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በማንኛዉም የፌዴራልም ሆነ የክልል ፍርድ ቤት ላይ በአስገዳጅነት ተፈጻሚ እንደሚሆን ተደንግጓል። በያዝነዉ ጉዳይ አመልካች ትከላከል የተባለችባቸዉ ተደራራቢ ክሶች በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 31/1 እና 32/1 ስር በመሆኑ እነዚህ ድንጋጌዎች የሚያስቀጡት እስከ ሦስት ዓመት ቀላል እስራት ሳይሆን ከሦስት ዓመት እስከ ሰባት ዓመት እና ከሦስት ዓመት አስከ አስር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት በመሆኑ መነሻ ቅጣታቸዉ ከአራት ዓመት በታች በሆነ ጽኑ እስራት የሚያስቀጡ ናቸዉ።ሆኖም ከላይ በተገለጸዉ መሰረት በሰ/መ/ቁጥር 182050 እና 183488 ላይ በአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 4/1 ሁለተኛ ዐረፍተ ነገር ላይ ለተደነገገዉ ከተሰጠዉ

አስገዳጅ ትርጉም መሠረት ሁለቱም ተደራራቢ ክሶች ላይ የተደነገገዉ ቅጣት ሲደመር ከአስር ዓመት በላይ የሚያስቀጡ ናቸዉ፡፡

ስለሆነም ተጠቃሹ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ጸንቶ እያለ ለአመልካች የዋስትና መብት የሚያስጠብቅ ዉሳኔ መስጠት ስለማይቻል የክልሉ ፍርድ ቤቶች *የአመልካችን* የዋስትና መብት ጥያቄ ዉድቅ በማድረግ በሰጡት ዉሳኔ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የሕግ ስህተት ባለመፈጸሙ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

የጎፋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 10891 ላይ በቀን 30/11/2011ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 004723 ላይ በቀን 07/12/2016 ዓ.ም የሰጠዉ ፍርድ እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 004815 ላይ በቀን 22/12/2016 ዓ.ም የሰጠዉ ትእዛዝ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 መሰረት ጸንተዋል፡፡

## ትዕዛዝ

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ለግራ ቀኙም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
## የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 273144

ታህሳስ 21 ቀን 2017ዓ/ም

**ዳኞች፡-** ገበየሁ ፈለቀ

ሀፍዝ አባጀማል

ደረጀ አያና

ደጀኔ አያንሳ

ብርሃኑ መንግሥቱ

**አመልካች፡-** አቶ አለማየሁ ኃ/ጊዮርጊስ

**ተጠሪ፡-** የፍትህ ሚኒስቴር ዐቃቤ ሕግ

ለምርመራ የተቀጠረው መዝገብ ተመርምሮ ተመርምሮ ቀጣዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ አመልካች ሚስት የሆኑት ወ/ሮ ዓለምፀሐይ ስላሱ የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 539/1(ሀ) ተላልፈው መስከረም 3 ቀን 2017 ዓ.ም የግዲያ ወንጀል ፈጽመዋል በሚል ክስ በመሠረተበት ጉዳይ የቤት ሠራተኛው የሆነችውን ግለሰብ ቅጣቱ በአንቺ ስለማይከብድ የሚች ገዳይ እኔ ነኝ በይ በማለት በተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች በመደለል እና የካሜራውን ዱካ በማጥፋት የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 445 ተላልፈዋል በሚል በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ክስ ቀርቦባቸው አመልካች ተላልፈዋል የተባሉት ድንጋጌ በቀላል እስራት ወይም በመቀጮ ስለሚያስቀጣ ዋስትናን የሚያስከልክል አለመሆኑን ጠቅሰው አስተዳደሪ እና የሕጻነት ልጆች አባት ስለሆኑ የዋስትና መብት እንዲከበርላቸው ጠይቀዋል፡፡ ዓቃቤ ሕግም በቀረበው የዋስትና ጥያቄ ላይ በሰጡት መልስ አመልካች የተከሰሱበት የሕግ አንቀጽ ዋስትና የሚያስከለክል ባይሆንም በግዲያ ወንጀል የተከሰሱት ባለቤታቸው በሕግ ተጠያቂ እንዳይሆኑ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ማስረጃ ለማጥፋት የሞከሩ በመሆኑ በዋስትና ቢወጡ 1ኛ የዐቃቤ ሕግ ምስክርንና ሌሎችንም ስለሚያባብሉ የዓቃቤ ሕግ ማስረጃ እስክሰማ ድረስ የዋስትና ጥያቄው ውድቅ እንዲሆን ጠይቀዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የተጠሪ ክርክር አመልካች ከተከሰሱት ወንጀል አንጻር በዋስትና ቢወጡ የዓቃቤ-ሕግ ምስክሮችን ያባብላል በሚል በመሆኑ ዋስትና መብት ቢሆንም የወንጀሉ ተጎጂዎች ፍትሕ ማግኘት ያለባቸው በመሆኑና ሕፃናት መኖር የዋስትና ጥያቄውን ለመመርመር ያስችል እንደሆነ እንጅ እራሱን ችሎ ዋስትና ለመፍቀድ ምክንያት ስለማይሆን ክሱ ባለበት ደረጃ አመልካች በዋስ ቢወጣ ባለቤቱ የሆነችው 1ኛ ተከሳሽ በወንጀል እንዳትጠየቅ ተጠሪ እንደሚለው የዓቃቤ ሕግ ምስክሮችን ሊያባብል ይችላል የሚል ግምት ወስዶ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 67/ሀ መሠረት የአመልካችን በዋስትና የመውጣት ጥያቄ በአብላጫ ድምጽ ውድቅ አድርጓል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎትም የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ የሚያስለውጥ በቂ ምክንያት አልተገኘም በማለት የይግባኝ አቤቱታውን ውድቅ አድርጎታል፡፡

የሰበር አቤቱታው አመልካች ያቀረቡት የዋትና ጥያቄ ውድቅ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል በሰበር ለማስለወጥ ሆኖ የአቤቱታው ይዘት በአጭሩ፡- ዋስትና ለዜጎች ሁሉ የተፈቀደ መሠረታዊ መብት በመሆኑ ግልጽ የሕግ ገደብ በሌለበት ልነፈግ እንደማይገባ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት እና ኢትዮጵያ ተቀብላ የሀገርቱ የሕግ አካል ባደረገቻቸው ዓለምአቀፍ ስምምነቶች በግልጽ ስለተደነገገ ልዩ ሁኔታው በጠባቡ ሊረጎም ሲገባው አመልካች የተከሰሱበት የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 445 ደንጋጌ ዋስትናን የማያስከለክል ሲሆን በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕጉም ልዩ ክልከላ በሌለበት አመልካች ሊያባብል ይችላል የተባለችው የዐቃቤ ሕግ 1ኛ ምስክር የሆነችው ግለሰብም በወንጀል ተጠርጥራ በአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን በእስር ላይ ስለሚትገኝ አመልካች ግለሰቧን አግኝቶ ሊያባብል የሚችልበት ዕድል የሌለ ከመሆኑም በላይ ግለሰቧ በቀዳሚ ምርመራ የምስክርነት ቃሏን ስለሰጠች የሚጠፋ ማስረጃ በሌለበት የአመልካችን እንደንጹሕ የመቆጠር መሠረታዊ መብት የሚጥስ ከመሆኑም በተጨማሪ ዕድሜያቸው ከ5 ዓመት በታች የሖኑትን የአመልካች ልጆችን መብትና ጥቅም የሚጎዳ የሕገ-መንግስቱን አንቀጽ 36/2፤13/2 ፤እንዲሁም የሰበር ሰሚ ችሎቱ በሰበር መዝገብ ቁጥር 177216 የሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሚቃረን መሠረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 6/1 መሠረት ለሰበር ሰሚው ችሎቱ የተመራው የሰበር አቤቱታ በሰበር ሰሚ ችሎቱ ተመርምሮ ምስክር ያባብላሉ ወይም ያጠፋሉ በሚለውን አመልካች የተከሰሱበት የወንጀል ድርጊት መቋቋሚያ ፍሬ ነገር የሆነውን የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 445 መሠረት በማድረግ የሥር ፍርድ ቤቶች የአመልካችን የዋስትና መብት የመንፈጋቸውን አግባብነት ከሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 19/6፤ ከወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 67/ሐ፤እንዲሁም አመልካች ሚስት የሆኑት የሥር 1ኛ ተከሳሽም በእስር ላይ የሚገኙ ከመሆኑ አንፃር የአመልካች የዋስትና መብት መከልከል በሕፃናት ልጆቻቸው መብትና ጥቅም ላይ ሊደርስ የሚችለው ጉዳት ከግምት ውስጥ ገብቶ መሆን/አለመሆኑን በሰበር መዝገብ ቁጥር 177216 ላይ ከተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ጋር አገናዝቦ ለመመርመር ያስቀርባ ተብሎ ተጠሪ ተከታዩን መልስ ሰጥተዋል፡፡ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 67 ሥር የተመለከቱ ምክንያቶች መሟላት አለመሟላታቸውን ፍርድ ቤቶች ከሁኔታዎች አንፃር መዝነው እና አከባቢያዊ ነገሮች ተመልክተው ግምት የሚወሰድበት ለሥር ፍርድ ቤቶች የተተው ጉዳይ እንጅ እንደ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተወስዶ በሰበር ሊታረም እንደማይገባ በሰበር መዝገብ ቁጥር 67874 አስገዳጅ የሕግ ትርጉም

የተሰጠ መሆኑን፤ በአመልካች በተገባላት የተስፋ ቃል የግዲያ ወንጀል እንደፈፀመች አድርጋ ለፖሊስ ቃሏን የሰጠችው ግለሰብ በምርመራ መዝገቡ ወደ ምስክርነት እንድትቀየር ስለተደረገ በእስር ላይ ስለማትገኝ አመልካች በዋስትና ቢወጣ ይህችንም ሆነ ሌሎች ማስረጃዎችን ሊያጠፋ ስለሚችል የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች እስኪሰሙ ድረስ የዋስትና መብቱ መነፈጉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሚያስብል አለመሆኑን፤ በቀዳሚ ምርመራ መዝገብ ላይ የተሰጠው ምስክርነት ተቀባይነት የሚኖረው ምስክሩ ከሀገር ከወጣ ወይንም ከሞተ ብቻ መሆኑ እየታወቀ ምስክሯ ቃሏን ሰጥታለች በሚል ምክንያት ብቻ የዋስትና መብቱን መፍቀድ ተገቢ አለመሆኑንና የሕጻናት መብትና ጥቅም የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ ጋር ተጣጥሞ ካልተተረጎመ የሰበር ሰሚ ችሎቱ የሚሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በሀገራች የሚገኙ ሁሉንም ፍርድ ቤቶች የሚያስገደድ ከመሆኑ አንፃር ሕፃናት ልጆች ያላቸው ተከሳሾች ሁሉ ዋስትና በሕግ እስካልተከለከ ድረስ የዋስትና መብታቸው ሊነፈግ አይገባል ወደ ሚል ድምዳሜ ሊያደርስ ስለሚችል የሥር ፍርድ ቤቶች የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች እስኪሰሙ ድረስ ብቻ የአመልካች የዋስትና መብት መንፈጋቸው የሕፃናቱ መብት ታሳቢ ያደረገ መሆኑን፤ በሰበር መዝገብ ቁጥር 177216 የተሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ በወጀል ሕጉ አንቀጽ 192-197 የተመለከቱ ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ በፈፀመው የወንጀል ደርጊት ማረሚያ ቤት ያለን ሰው በሕጻናት ልጆቹ ላይ የሚደርሰውን ቁሳዊም ሆነ የሕሊና ጫናን ለማስቀረት ፍርድ ቤቶች ሕገ-መንግስታዊ ግዴታ ስላለባቸው ቅጣቱ እንዲታገድ ማድረግ ተገቢ መሆኑን የሚያመለክት ሲሆን አመልካች በዋስትና ቢለቀቅ ፍትሕ ማግኘት የሚፈልጉ ቤተሰቦች ያሉ በመሆኑና የአመልካች ሕፃናት ልጆች ሊደርስባቸው የሚችለውን ጉዳት ከግምት ውስጥ በማስገባት በተፋጠነ ሁኔታ የዓቃቤ-ሕግ ምስክሮች እስክሰሙ ደረስ ላለው ጊዜ ብቻ የአመልካች የዋስትና መብት በመነፈጉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚያስብል ባለመሆኑ የሰበር አቤቱታው ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ታህሳስ 4 ቀን 2017 ዓ.ም ያቀረቡት ሁለት ገጽ የመልስ መልስ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለ መልኩ የተመለከተው የግራ ቀኝ ክርክር እና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ውሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንፃር የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ማንም ሰው በተከሰሰበት ወንጀል ክሱ በይፋ በሚሰማበት ግልጽ ችሎት የመከላከል መብቱ በሕግ ተጠብቆለት ጥፋተኛ መሆኑን እስክረጋገጥ ድረስ እንደጥፋተኛ ያለመቆጠር መብት ያለው መሆኑን የሰብዓዊ መብቶች ሁሉ-ዓቀፍ መግለጫ(Universal Declaration of Human Right) አንቀጽ 11/1 ፤የሲቪልና የፖለትካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን (Internationa Convention on Civil and Political Rights) አንቀጽ 14/2፤እንዲሁም የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አዋጅ ቁጥር 1/1987 አንቀጽ 20/3 ድንጋጌዎች ያመለክታሉ፡፡ ዋስትና የተጠሪጣሪው ወይም የተከሳሹ ነፃ እንደሆነ የመቆጠር መብት መገለጫ አንዱ ባሕሪ ነው፡፡ የሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 19/6 የተያዙ ሰዎች በዋስ የመፈታት መብት ያላቸው ቢሆንም በሕግ በልዩ ሁኔታ በተደነገገ ጊዜ ዋስትና ሊከለከል እንደሚችል

ማስ ታወሻ፡ - ይህ የ ሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነ ድ ለ ጥና ትና ምር ምር ሥራ ወይምለ ግንዛቤ እን ጂ

ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገ ለግልም!

ያመለክታል፡፡ ይህን መሠረታዊ ሕገ-መንግስታዊ መብት ፍርድ ቤቶች የማስከበር ግዴታ እንዳለባቸው ከሕገ- መንግስቱ አንቀጽ 13/2 ድንጋጌ መረዳት ይቻላል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎትም የተያዘን ሰው በዋስትና መፍታት መርህ በመሆኑ በሰፍው መተርጎም እንዳለበት በሰበር መዝገብ ቁጥር 31734 (በቅጽ 7 እንደታተመው) አስገዳጅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የቀረበውን የዋስት ጥያቄ በፍርድ ቤት ተቀባይነት ሊያጣ ከሚችልባቸው ነገሮች ውስጥ የመጀመሪው ዋስትናን የሚያስከለክሉ ልዩ ሁኔታዎች መኖር ሲሆን ሁለተኛው በሕጉ ዋስትና የተፈቀደ ቢሆንም በፍርድ ቤት ተቀባይነት ሊያጣ የሚችል አግባብን የሚመለከት ነው፡፡ ዋስትና ሊከለከል የሚችልባቸው ሁኔታዎች በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 67 ሥር ተመልክቷል፡፡ የተያዘ ሰው ምስክሮችን ያባብላል ወይም ሌሎች ማስረጃዎችን ያጠፋል ተብሎ ስገመት የዋስት መብቱን ሊነፈግ እንደሚችል የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 67/ሐ ይደነግጋል፡፡ ይህ የሚሆነው የወንጀል ጉዳዩ በምርምራ ላይ የሚገኝ ሲሆንና መርማሪ ፖሊስ ለወንጀል ምርመራ የሚረዱ እና ያልተያዙ ማስረጃዎች ወይም ስለወንጀሉ የሚያውቁ ምስክሮች ለፖሊስ የምስክርነት ቃላቸውን ያልሰጡ እንደሆነ ነው፡፡ (የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 59 እና 30 ድንጋጌን ይመለከቷል)፡፡ መርማሪ ፖሊስ ይህን ሥራውን እንዳጠናቀቀ ተጠርጣሪውን በማረለፍያ ቤት ለማቆየት የሚያበቃ ሌላ ምክንያት ከሌለ የተያዘው ሰው ፍርድ ቤት በሚወስነው የዋስትና ዓይነትና መጠን ከእስር ይለቀቃል፡፡

በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ እ. ኤ.አ ታህሳስ 20 ቀን 1989 ዓ/ም ፀድቆ መስከረም 2 ቀን 1990 ዓ/ም በሥራ ላይ የዋለዉ ኢትዮጵያም በአዋጅ ቁጥር 10/1984 ተቀብላ ያፀደቀችዉ የሕፃናት መብት ስምምነት(Convention on the Right of Child) አንቀጽ 3/1፤የአፍርካ ሕፃናት መብቶችና ደህነት ቻርተር(African Charter on the Right and Welfare of the Child) ኢትዮጵያ በአዋጅ ቁጥር 283/1994 ተቀብላ ያፀደቀችው አንቀጽ 4/1 እንዲሁም የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 36/2 በመንግስት ተቋምም ሆነ በማንኛውም ሰው የሚከናወን ሕጻናትን የሚመለከት ሥራ ለሕፃናቱ ደህንነት(ጥቅም) ቅድሚያ ሊሰጥ እንደሚገባ ይደነግጋሉ፡፡ በሌላ በኩል የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎትም አግባብነት ያላቸውን ሕጎችን በመመርመር የሕፃናት መብት እና ጥቅም ለማስከበር በቀደምትነት መርህ የሕፃናት ጥቅምና ደህነት (best interest of the child) መሆኑን በሰበር መዝገብ ቁጥር 23632፤ 35710 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት አስገዳጅ ውሳኔ ሰቷል።

በተያዘው ጉዳይ አመልካች በሰው ነፍስ ግዲያ ወንጀል የተጠረጠሩት ባለቤታቸው ፈጽመዋል በተባለው የወንጀል ድርጊት ተጠያቂ እንዳይሆኑ የምርመራ ሥራውን ለማሳሳት የቤት ሠራተኛቸው የነበረችውን ግለሰብ የሚች ገዳይ እኔ ነኝ ብላ ለፖሊስ ቃሏን እንዲትሰጥ በማባበል የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 445 ተላልፈዋል በሚል የተጠረጠሩ ስለሆነ አመልካች ከተከሰሱበት ወንጀል ልዩ ባሕርይ አንፃር የዋስትና መብታቸው ብከበርላቸው የዐቃቤ ሕግን ምስክር በማባበል ማስረጃ ሊያጠፉ ይችላሉ የሚል ግምት

መውሰድ የሥር ፍርድ ቤቶች ሥልጣን(Discretion) ቢሆንም በአመልካች ላይ ምስክር ልትሆን የሚትችለው ግለሰብ ማንነት ታውቆ ለፖሊስ የምስክርነት ቃሏን ሰጥታ ክሱ ለፍርድ ቤት ቀርቦ እያለ ምስክሯ ለፖሊስ የሰጠችውን የምስክርነት ቃል አመልካች በምን አግባብ ሊያስቀይራት እንደሚችል በተጠሪ በኩል ግልጽ ክርክር ባልቀረበበት አመልካች ምስክር ሊያባብሉ ይችላሉ ተብሎ የዋስትና መብታቸው መነፈጉ የጥፋተኝነት ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት አመልካች በተከሰሱበት ወንጀል እንደጥፋተኛ ያለመቆጠር መብታቸውን የሚጥስ ከመሆኑም በላይ እናት እና አባታቸው በሕግ ቁጥጥር ሥር ያሉትን ዕድሜያቸው ከ5(አምስት) ዓመት በታች የሖኑትን የሥር 1ኛ ተከሳሽ እና አመልካች በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 219 መሠረት አስተዳዳሪና ሞግዚት የሚሆኗቸውን ሕፃናት ጥቅምና ደህነት (best interest of the child) ያለከበረ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ቀጣዩ ተወስኗል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው የወንጀል ችሎት መዝገብ ቁጥር 272430 ህዳር 19 ቀን 2017 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ እና ትዕዛዝ ፤እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 328311 ህዳር 9 ቀን 2017 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ እና ትዕዛዝ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 9/1(ለ) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በሌላ ወንጀል የማይፈለጉ ከሆነ ለብር 10,000.00(አሥር ሺህ) የሚበቃ ዋስትና በማቅረብ ወይንም ገንዘቡን በማስያዝ የቀረበባቸውን ክስ ከማረሚያ ቤት ውጪ ሆነው እንዲከታተሉ ተወስኗል፡፡
3. አመልካች የ10,000.00(አሥር ሺህ) ብር ዋስትና ማቅረባቸው ወይንም ገንዘቡን ማስያዛቸው ሲረጋገጥ ከቂልጦ ማረሚያ ቤት እንዲለቀቁ ታዟል፡፡ ይጻፍ፡፡
4. የውሳኔው ትክክለኛ ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች እና ለቂልጦ ማረሚያ ቤት ይድረስ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ውሳኔ አግኝቶ ስለተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ሰ/ወ

# በጥር ወር 2017 የተወሰኑ
# 22 የሰበር ችሎት ውሳኔዎች

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
## የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መ/ቁ/245981

ጥር 27 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች፡ ብርሃኑ አመነው

ሸመክት አሰፋ

በእውቀቱ በላይ

መላኩ ካሳዬ

ማርታ ተካ

አመልካቾች -1. አቶ አበራ ነጋሽ ደምሴ

2. አቶ አዱኛ ነጋሽ ደምሴ

3. አቶ ብርሃኑ ነጋሽ ደምሴ

4. ወ/ሪት አበባ ነጋሽ ደምሴ

5. ወ/ሪት ጌጤነሽ ነጋሽ ደምሴ

6. አቶ ግርማ ደምሴ ፉሪ

ተጠሪዎች- 1. ቦሌ ቡልቡላ ደብረ መድኃኔዓለም ቤ/ክርስቲያን

2. የቦሌ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ፅ/ቤት

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

**ማስታወሻ፡** - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገ ለግልም!

መዝገቡ ለሰበር ችሎት የቀረበዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ማጽናት በመ/ቁ302527 ላይ በቀን 23/05/2015ዓ.ም የሰጠዉ ብይን የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል በሰበር ችሎት እንዲታረም አመልካቾች ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ ነዉ፡፡

ጉዳዩ የመሬት ባለይዞታነት መብት የሚመለከት ሲሆን በስር ፍርድ ቤት የአሁን አመልካቾች ከሳሽ ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡አመልካቾች በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ131415 ባቀረቡት ክስ በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 12 ክልል ውስጥ የሚገኝ ከ1-5 የተዘረዘሩት አመልካቾች ወላጅ አባት እና የ6ኛ አመልካች ወንድም የሆኑት በጋራ ይዘው ይጠቀሙበት የነበረ በግምት ከ60,000 ካ.ሜ ያላነሰ ስፋት ያለው አዋሳኞቹ በክሱ የተጠቀሰ ይዞታ ለረጅም ጊዜ ግብር እየገበሩበት ሲጠቀሙ የቆዩ ቢሆንም ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ በ1ኛ ተጠሪ ቤተክርስቲያን የሰበካ ጉባኤ ኮሚቴ አባላት አማካኝነት የሀይማኖት ተቋሙ በማህበረሰቡ ዘንድ ያለውን መፈራት እና መከበር በመጠቀም የአመልካቾችን ይዞታ ለመቃብር ቦታ በሚል ምክንያት በመውሰድ ከፋፍሎ እና ሼዶችን ገንብቶ ለጋራዥ እና ሌሎች የንግድ አገልግሎቶች ኪራይ ገቢ እየሰበሰበ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንዲሰራ በማድረግ በህገወጥ መንገድ ይዞት ይገኛል፡፡ስለሆነም ለ1ኛተጠሪ የተሰጠው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ተሰርዞ ለአመልካቾች እንዲመለስ ሲሉ ዳኝነት መጠየቃቸዉን መዝገቡ ያሣያል፡፡

1ኛተጠሪም መቃወሚያና አማራጭ መልስ ያቀረበች ሲሆን በመልሱም 1ኛተጠሪ በህግ አግባብ ያገኘችውን የይዞታ ባለቤትነት ካርታ ለማስተባበል የሚበቃ ማስረጃ እንዲሁም ቦታውን በህግ አግባብ ይዘውት እንደነበር አንድም ማስረጃ አላቀረቡም፤የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የይዞታ አገልግሎት አስተዳደር ለዕምነት ተቋማት ይዞታ ማረጋገጥን አስመልክቶ ባወጣው መመሪያ ቁጥር 2/2004 መሰረት ደብሩ ከተመሰረተበት ከ27 ዓመት ጀምሮ በይዞታው ስር አድርጎ ለቀብር አገልግሎት ያዋለው መሆኑ በህግ አግባብ ተለይቶ ተጣርቶ የባለቤትነት ምስክር ወረቀት የተሰጠ በመሆኑ የአመልካቾች አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግል በማለት ተከራክረዋል፡፡2ኛ ተጠሪ ባቀረበዉ መልስ አመልካቾች ያቀረቡት የሰነድ ማስረጃ በ2ኛ አመልካች ስም ግብር እንደተከፈለ የሚያሳይ ሲሆን ክስ ለቀረበበት ይዞታ የገበሩ ስለመሆናቸው የማያረጋግጡ ከመሆኑም በላይ የግብር ደረሰኝ ባለሀብትነትን ቀርቶ ባለይዞታነትን እንኳን የማረጋገጥ ብቃት የለውም፤ስለሆነም አመልካቾች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/33(2) መሰረት ያላቸውን መብትና ጥቅም አግባብነት ባለው ማስረጃ ስላላረጋገጡ ክሱን በብይን ውድቅ እንድደረግ በማለት መከራከሩን መዝገቡ ያሣያል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከግራ ቀኙ ክርክር በመነሳት ህጋዊ የይዞታ መብት ያለው ማነው? በዚህ ቦታ ላይ ለ1ኛ ተጠሪ የተሰጠ ካርታ በአግባቡ የተሰጠ ነው ወይስ አይደለም? 1ኛተጠሪ ለአመልካቾች ሊያስረክብ ይገባል ወይስ አይገባም የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ የግራቀኙን ምስክር ሰምቶ እና ስለይዞታዉ ከክፍለ ከተማ መረጃ በመጠየቅ ይዞታው በ1988 ጂ.አይ.ኤስ ወይም በ1997

ዓ.ም የመስመር ካርታ ባይታይም የ2ኛ ተጠሪ ምስክር እንዳስረዱት በቦታው ላይ በወቅቱ ተሂዶ ሰርቬየሮች ባመጡት ልኬት መሰረት ተገቢውን ሂደት ተከትሎ ካርታው ተዘጋጅቶ ለ1ኛ ተጠሪ የተሰጠ መሆኑን በመመስከራቸው ለ1ኛ ተጠሪ የተሰጠው ካርታ ሊሰረዝ አይገባም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካቾች በውሳኔው ላይ ይግባኝ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ስ/ሕ/ቁ/337 መሰረት ሰርዟል፡፡ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ነዉ፡፡

የአመልካቾች ጠበቃ ሚያዝያ 18 ቀን 2015ዓ.ም ጽፎ ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ለ1ኛተጠሪ የተሰጠው ካርታ ከህግና ከመመሪያ ውጭ ነው፤ ካርታው የኃይማኖት ተቋማት የይዞታ ማስረጃ አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 2/2004 መሰረት የተሰጠ ስለመሆኑ ማረጋገጫ አልቀረበም፤1ኛ ተጠሪ ሁለት ይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ያላት ሲሆን የመጀመሪያው በቁጥር ቦሌ 12/39/1/8/16444/28318/01 በቀን 26/12/2007 ዓ.ም የተሰጠ ሲሆን 2ኛው የካርታ ቁጥር ቦሌ/3/53/2/4/16445/00 የተሰጠበት ቀን 08/12/2004ዓ.ም የሆነው በህገወጥ መንገድ የተገኘ እና ተቀባይነት የሌለው ነው፤ሁለቱንም ካርታዎች ስናስተያይ ቁጥራቸው ተካታታይ ማለትም 16444 እና 16445 ሲሆን በ2004ዓ.ም የተሰጠው ካርታ መጨረሻ ቁጥር 45 ሆኖ በ2007ዓ.ም የተሰጠው ደግሞ የመጨረሻ ቁጥር 44 ነው፤ካርታ በቅድም ተከተል የሚሰጥ ከመሆኑ አንፃር 2007ዓ.ም የተሰጠው ካርታ ከ2004ዓ.ም ከተሰጠው ካርታ ቁጥር የሚቀድምበትም ሆነ ተከታታይ የሚሆንበት አግባብ የለም፤የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቦሌ ምድብ 4ኛ ፍትሓብሄር ችሎት በኮ/መ/ቁ/132036 በቀን 30/10/2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት ካርታው ያለአግባብ የተሰጠ መሆኑን በመግለፅ ካርታው እንዲመክን ውሳኔ ሰጥቶ በሰበር ፀንቷል፤የስር ፍ/ቤት ገለልተኛ ያልሆኑ ህገወጡን ካርታ አዘጋጅተው በፈረሙ እና ራሳቸውን ከወንጀል ተጠያቂነት ለማዳን ጥረት በሚያደርጉ ግለሰቦች የምስክርነት ቃል ብቻ መሰረት አድርጎ የሰጠው ውሳኔ አግባብነት የለውም፤ አከራካሪው ይዞታ የአመልካቾች ስለመሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ ለህዝብ ጥቅም የመውረስ ውሳኔ ሳይሰጥ፤ ካሳ፤ ምትክ ቦታ፤ ቅድሚያ የማልማት መብት ሳይከበርና የልማት ተነሺ ማቋቋሚያ ሳይሰጥ ከህግና መመሪያ ውጭ አርሶ አደርን ከይዞታው በማፈናቀል 2ኛ ተጠሪ ለ1ኛ ተጠሪ የይዞታ ማረጋገጫ የሰጠበት ሁኔታ መመሪያ ቁጥር 2/2004 አንቀጽ 6 ስር ካሉት መስፈርቶች አንዱንም አያሟላም፤ ስለሆነም ህገ-ወጥ መሆኑ የስር ፍ/ቤት ሀሰተኛ ሰነድ መሰረት አድርጎ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ውሳኔው ተሽሮ ይዞታውን ለቆ እንዲያስረክቡን እንዲወሰን በማለት አመልክተዋል፡፡

የሰበር ችሎቱ አቤቱታቸዉን መርምሮ ክርክር የተነሳበት ይዞታ ቀደም ሲል የአመልካቾች አባት ለእርሻ ሲጠቀሙበት እንደነበር የግብር ደረሰኞች እና ምስክሮች እንዲሁም በአርሶ አደር ኮሜቴ ተጣርቶ የቀረበውን አስተያየት መኖሩ እና ክፍለ ከተማ ይህንኑ መግለጫ ለፍርድ ቤት ማቅረቡን በሌላ በኩል ለ1ኛ ተጠሪ ካርታ የተሰራበት አግባብ የሚያሳዩ ሰነዶችን አለማግኘቱ ክፍለ ከተማ

አስተዳደር መግለፁን ጠቅሶ እና በዚህ ረገድ መመሪያ ቁጥር 2/2004 መሰረት ተድርጎ አልተመረመረም በሚል አመልካቾች ካቀረቡት አቤቱታ አኳያ የስር ፍርድ ቤት ለጉዳዩ አወሳሰን ተገቢውን ጭብጥ መያዝ አለመያዙ እና በማስረጃ ምዘና ረገድ ሰነዶች እና የምስክሮች ቃል፤ከአስተዳደር አካል የቀረቡትን መግለጫዎች የመዘነበት አግባብ ከማስረጃ አቀባበልና ምዘና መርህ አኳያ ሰበር ችሎቱ በተለያዩ መዝገቦች በሰ/መ/ቁ47252፤ 47551 እና በሌሎች መዝገቦች የሰጠውን ትርጉም ያገናዘበ መሆን አለመሆኑን እና የተፈፀመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን ለመመርመር ተጠሪዎች መልሳቸውን እንዲያቀርቡ አዟል፡፡

1ኛ ተጠሪ በህዳር 23 ቀን 2017 ዓ.ም በተጻፈ መልስ በካርታ ቁጥር ቦሌ/3/53/ 2/4/16445/00 የተሰጣት ካርታ እንዲመክን ተወስኗል የተባለው ሀሰት ነው ካርታው አልመከነም፤በካርታ ቁጥር ቦሌ/3/53/2/4/16445/00 እንዲሁም በካርታ ቁጥር ቦሌ 12/39/1/8/16444/28318/01 ህጋዊ ይዞታ ያላት ስለመሆኑ በተለያዩ የፍርድ ቤት መዝገቦች በውሳኔ ተረጋግጧል፤አመልካቾች በይዞታው ላይ መብትና ጥቅማቸውን አላረጋገጡም፤ከሁለቱ አመልካቾች በቀር ሁሉም አመልካቾች የግብር ደረሰኝ ያላቀረቡና ደረሰኞቹም ክርክር ባስነሳው ይዞታ ላይ መሆኑን የሚያስረዱ የወራሽነት ማስረጃ ያልቀረበበት ነው፤ከአርሶ አደር ኮሚቴ የተላከው ማስረጃ በአርሶ አደር መኖሪያ ቤትና የከተማ ግብርና መጠቀሚያ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ መመሪያ ቁ/20/13 ተከትሎ ያልተሰጠ በምስክርም ያልተረጋገጠ ነው፡፡በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ የህግና የፍሬ ነገር ስህተት የሌለበት በመሆኑ እንዲፀና በማለት ተከራክራዋል፡፡2ኛ ተጠሪ በበኩሉ በታህሳስ 7 ቀን 2017ዓ.ም በተጻፈ መልስ አመልካቾች በይዞታው ላይ አርሶ አደር ብንሆንም ያለአግባብ ተፈናቅለናል ሲሉ ያቀረቡት ቅሬታ ተገቢነት የለውም፤አስቀድመው በክሳቸው ዳኝነት ያልጠየቁበት ነው፤ለ1ኛ ተጠሪ የተሰጠው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ አስቀድሞ ለቤተክርስቲያኗ የተሰጠ እና በመቀጠልም ለቀብር አገልግሎት የተሰጠ የይዞታ ማረጋገጫ ነው፤ይህም በመመሪያ ቁጥር2/2004 አንቀፅ 6 እና 10 በተደነገገው መሰረት ነው፤ይዞታው በ1997 የመስመር ካርታ እና በጂ.አይ.ኤስ ላይ የማይታይ ቢሆንም 1ኛ ተጠሪ ካርታ እንዲሰጣቸው ጥያቄ አቅርበው ካርታ ተዘጋጅቶ የተሰጠ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ መሬት ልማት እና አስተዳደር ቢሮ በቀን 3/10/2004 ለስር ፍርድ ቤት በሰጠው ምላሽ አረጋግጧል፡፡በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍበት የህግም ሆነ መሰረታዊ የማስረጃ ስህተት ያልተፈፀመበት በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲፀና ሲል ምላሹን አቅርቧል፡፡አመልካቾች አቤቱታቸዉን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል ፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ያስቀርባል ሲባል የተያዘውን ጭብጥ ከግራቀኙ ክርክር፤በስር ፍርድ ቤት በማስረጃ ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር እና ከተገቢው የህግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡እንደመረመርነዉ የአመልካቾች የዳኝነት ጥያቄ በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 12 ክልል ውስጥ የሚገኝ ከ1-5 የተዘረዘሩት አመልካቾች ወላጅ አባት እና የ6ኛ

አመልካች ወንድም የሆኑት በጋራ ይዘው ይጠቀሙበት የነበረ በግምት ከ60,000 ካ.ሜ ያላነሰ ስፋት ያለው መሬት ላይ ለ1ኛ ተጠሪ ከህግ አግባብ ዉጪ የተሰጠ ካርታ ቁጥር ቦሌ/3/53/2/4/16445/00 ይዞታ ማረጋገጫ እንዲመክን እና መሬቱን እንድትለቅ የሚል ነዉ፡፡

በኢ.ፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40/3/ እንደተደነገገዉ የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት የባለቤትነት መብት የመንግሥትና የሕዝብ እንደሆነ፤መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት ነዉ፡፡ይሁንና ሰዎች መሬትን የመጠቀም መብት እንዳለቸዉ እና የመሬት ባለይዞታነት መብት የሚገኝበት ስርዓት በዝርዝር ህጎች የሚወሰን መሆኑም ተመልክቷል፡፡ይህንን ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌ ለማስፈጸም የከተማም ሆነ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም በተመለከተ በፌዴራል እና በክልል መንግሥታት የወጡ ሕግጋት እንደሚያስገነዝቡት መሬት በግለሰብ ባለቤትነት ሊያዝ የማይችል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ግለሰቦች ወይም ሌሎች በህግ የሰዉነት መብት የተሰጣቸዉ አካላት መሬት የመጠቀም ይዞታ መብት የሚያገኙበት ስርዓት እና በመሬቱ ላይ በጉልበታቸዉ፣በመፍጠር ችሎታቸዉ ወይም በካፒታላቸዉ ባፈሩት ማንኛውም ተጨባጭ የሆነና የተጨባጭነት ጠባይ በሌለዉ ንብረት ላይ የባለቤትነት መብት እንዳላቸዉ ተመልክቷል፡፡

የአንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤት ነኝ የሚል ሰዉ የንብረቱ ባለቤት እንደሆነ የሚገመተዉ ንብረቱን በሕጋዊ መንገድ በስሙ አስመዝግቦ የባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ወይም ካርታ ሲይዝ እንደሆነ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1195/1 ስር ተደንግጓል፡፡በተመሳሳይ ስለከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባ በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 818/2006 አንቀጽ 42 ስር በተደነገገዉ መሰረት ተቃራኒ ሁኔታ መኖሩ እስካልተረጋገጠ ድረስ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 33/1 ስር በተደነገገዉ መሰረት የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት የተሰጠዉ ማንኛዉም ሰዉ በመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ላይ ለተጠቀሰዉ መሬት ባለይዞታ እና በመሬት ይዞታዉ ላይ ላረፈዉ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤት እንደሆነ ይቆጠራል፡፡በአስተዳደር አካል የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ የተሰጠዉ ሰዉ የዚሁ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀበት እንደሆነ የህግ ግምት የሚወሰድ ሲሆን ይህ የህግ ግምት በሌላ ማስረጃ ሊስተባበል እንደሚችል የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1196 ድንጋጌ ይዘት ያስገነዝባል፡፡ይኸዉም የምስክር ወረቀት የተሰጠዉ ከደንብ ዉጭ በሆነ አሰራር ወይም ስልጣን በሌለዉ አስተዳደር ክፍል ከሆነ ወይም በማይረጋ ጽሁፍ መሰረት የሆነ እንደሆነ ነዉ፡፡

ከክርክሩ እንደተገነዘበነዉ ለ1ኛ ተጠሪ የተሰጠዉ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ሁለት ሲሆን አንደኛዉ በካርታ ቁጥር ቦሌ 12/39/1/8/16444/28318/01 የተመዘገበ ሲሆን በዚህ ላይ መሬቱ የተገኘበት አግባብም ሆነ ይዞታ ማረጋገጫ የተሰጠበት አግባብ ላይ ግራቀኙን ያከራከረ ጉዳይ የለም፡፡ግራቀኙን ያከራከረዉ 2ኛዉ በካርታ ቁጥር ቁጥር ቦሌ/3/53/2/4/16445/00 የተመዘገበዉን መሬት የሚመለከት ሲሆን በዚህ መሬት ላይ መቃብር ቦታ፤ለጋራዥ እና ሌሎች አገልግሎቶች የሚሰጡ ቤቶች ያሉበት መሆኑን ክርክሩ ያሳያል፡፡አመልካቾች አጥብቀዉ የሚከራከሩት ይህ ቦታ አዉራሻቸዉ አቶ ነጋሽ

ደምሴ ለእርሻ እና ግጦሽ ሲጠቀሙበት እንደነበር እና በዉርስ የተላለፈላቸዉ ስለመሆኑ፤ነገር ግን 1ኛ ተጠሪ ያለአግባብ የያዘችዉ እና ካርታ ያለአግባብ የተሰጣት መሆኑን በመግለጽ ነዉ፡፡ይህ ክርክር የተነሳበት ቦታ ቀደም ሲል በአመልካቾች አዉራሽ የተያዘ እና ለእርሻ ሲጠቀሙበት እንደነበር በኋላም በዉርስ ለአመልካቾች የተላለፈ ስለመሆኑ ስር ፍርድ ቤት የቀረቡት የአርሶ አደር ኮሚቴ መግለጫ እና ሌሎችም ተያያዥ ማስረጃዎች መኖራቸዉ የሥር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ይዘት ያሣያል፡፡የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነትም ሆነ መሬት ባለይዞታነት መብት በሚመለከተዉ አካል የተረጋገጠ የምስክር ወረቀት በማቅረብ ማስረዳት እንደሚያስፈልግ እሙን ነዉ፡፡ይሁንና የምዝገባ ስርዓት በተሟላ ሁኔታ ባለመከናወኑ የሚነሱ ክርክሮችን አግባብነት ባላቸዉ ሌሎች ማስረጃዎችም ማስረዳት እንደሚቻል ሰበር ችሎቱ በተለያዩ መዝገቦች ዉሳኔ የሰጠበት ጉዳይ ነዉ፡፡(ሰበር መ/ቁ/ 33924 ቅጽ6፤36320 ቅጽ9 ላይ የታተመ) እና ሌሎች መዝገቦችን ይመለከታል፡፡

አመልካቾች ክስ ያቀረቡበት መሬት ቀደም ሲል አዉራሻቸዉ ለእርሻ ሲጠቀሙበት የነበረ እና በዉርስ የተላለፈላቸዉ መሆኑን መሰረት በማድረግ በካርታ ቁጥር ቦሌ/3/53/2/4/16445/00 የይዞታ ማረጋገጫ ለተጠሪ የተሰጠበት አግባብ ህጋዊነት ላይ ተቃዉሞ ማንሳታቸዉን መዝገቡ ያሣያል፡፡በዚህ ላይ የቀረበዉ መከራከሪያ በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡አንደኛዉ የሰነዱን ይዘት የሚመለከት ሲሆን ሁለተኛ መመሪያ ቁጥር 02/2004 ላይ የተደነገገዉን መስፈርት የሚመለከት ነዉ፡፡ይህንኑ በቅደም ተከተል ስንመለከት የሰነዱ ይዘት ጋር የተያያዘዉ መከራከሪያ በአንድ በኩል ካርታ ቁጥር ቁጥር ቦሌ/3/53/2/4/16445/00 የተዘጋጀዉ በ2004ዓ.ም ነዉ እየተባለ በ2007ዓ.ም ከተዘጋጀዉ ካርታ ቁጥር 12/39/1/8/16444/28318/01 ጋር ሲነጻጸር ቁጥር 1644 እና 1645 ተከታታይ እንዴት ሊሆን ቻለ የሚል ሲሆን ሁለተኛዉ መከራከሪያ ካርታ እንዲሰጥ ጥያቄ የቀረበዉ በቀን 07/12/2004ዓ.ም ሆኖ ካርታ ቁጥር ቦሌ/3/53/2/4/16445/00 በቀን 08/12/2004ዓ.ም ተዘጋጅቶ መሰጠቱ ሰነዱን ቅቡልነት የሚመለከት ነዉ፡፡ከላይእንደተገለጸዉ የማይንቀሳቀስ ንብረት የምስክር ወረቀት የማይረጋበትን ምክንያት አለ ብሎ የሚቃወም ሰዉ ማስረዳት ይጠበቅበታል፡፡ሰነዱ አጠራጣሪነቱ በታወቀ ጊዜ ጉዳዩ ከሚመለከተዉ አካል ተገቢዉን ማብራሪያና ማስረጃ መጠየቅ አስፋላጊ ነዉ፡፡ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ 27548(ቅጽ5 ላይ የታተመ) ዉሳኔ ይህንኑ የሚያጠናክር ነዉ፡፡በዚህ ረገድ የስር ፍርድ ቤት በጭብጥነት ይዞ ባለማጣራቱ ሰነዱ በህግ ፊት የማይረጋ መሆን አለመሆኑን በዚህ ሰበር ችሎት መመርመር አልተቻለም፡፡

ሁለተኛዉ የአመልካቾች መከራከሪያ የምስክር ወረቀቱ በመመሪያ ቁጥር 02/2004 መስፈርት አሟልቶ የተሰጠ መሆኑ አልተረጋገጠም የሚል ሲሆን ተጠሪዎች በበኩላቸዉ ክርክር የተነሳበት መሬት ላይ ለ1ኛ ተጠሪ ካርታ የተሰጠዉ መመሪያ ቁጥር 02/2004 መሰረት ነዉ በማለት ተከራክረዋል፡፡ስለዚህም በዚህ መመሪያ ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶች ባጭሩ መመልከት ተገቢ ነዉ፡፡መመሪያ ቁጥር

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

2/2004 በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለሚገኙ የሃይማኖት ተቋማት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ለመስጠት የወጣ የአሰራር መመሪያ መሆኑ ተመልክቷል፡፡

በዚህ መዝገብ ለተያዘዉ ክርክር አግባብነት ያለዉ የመመሪያዉ አንቀጽ 6 ይዘት ሲታይ፡

አንቀጽ 6.ከግንቦት 1988ዓ.ም እስከ መስከረም 9 ቀን 1998ዓ.ም የተያዙ ይዞታዎች ሆነዉ ነገር ግንህጋዊ የመሬት ባለይዞታነት ማረጋገጫ ካርታ ያላወጡትን የሃይማኖት ተቋማት ከዚህ በታች ከንኡስ አንቀጽ 6.1 እስከ 6.5 ድረስ ካሉት ቢያንስ አንዱን ሲያሟላና የተቀሩትን መስፈርቶችና መረጃዎችን ከንኡስ አንቀጽ (6.6 እስከ 6.9 ድረስ ያሉትን) ግን ሙሉ በሙሉ ሲያሟላ ለይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ብቁ ይሆናል።

6.1ከግንቦት 1988 እስከ መስከረም 1998ዓ.ም ድረስ በእምነት ተቋሙ ስም መብራት ወይም ዉሃ የገባበት ዉል ሲቀርብ ወይም

6.2 ቦታዉ በ1994 ወይም በ1997 ሳይን ማፕ ላይ የሚታይ ከሆነ ወይም

6.3 በወቅቱ በመንግስታዊ ተቋማት በቦታዉ ላይ የእምነት ተቋም እንዲመሰረት የተፈቀደበት አግባብ የሚያሣይ ሰነድ/ጽሁፍ ማስረጃ ሲቀርብ ወይም

6.4 ይዞታዉ በህጋዊ የይዞታ ባለቤትነት ማረጋጫ ካለዉ ሰዉ በግዥ ወይም በዉርስ ወይም በስጦታ የተገኘ ከሆነና ይዞታዉ የተላለፈበት ዉል ሲቀርብ ወይም

6.5 ይዞታዉ በዚህ ዘመን ስለመያዙ የሚያረጋግጡ ሌሎች ተገቢነት ያላቸዉ ህጋዊ የሰነድ ማስረጃዎች ሲቀርቡ እና

6.6 ቦታዉ አሁን በሃይማኖት ተቋም እጅ ስለመኖሩ ከወረዳዉ አስተዳደር ስራ አስኪያጅ ጽ/ቤት በደብዳቤ የተረጋገጠበት

6.8 በቦታዉ ላይ ምንም ዐይነት የይገባኛል ክርክር ወይም በፍርድ ቤት የተያዘ ጉዳይ የሌለዉ መሆኑ ሲረጋገጥ

6.8 ቦታዉን መንግስት ቀደም ብሎ (የሃይማኖት ተቋም ከመሰራቱ በፊት) በህጋዊ ሁኔታ ለሌላ ልማት እንዲዉል ያልሰጠዉ መሆኑ ሲረጋገጥ

6.9 የከተማዋን መዋቅራዊ ፕላን የማያፋልስ/የማይቃረን መሆኑ ሲረጋገጥ ይሆናል በማለት ዘርዝሯል፡፡

ስለዚህም ለክርክር ምክንያት የሆነዉ ካርታ የተሰጠበት አግባብ ከዚህ አኳያ መስፈርቱን ያሟላ መሆን አለመሆኑ መመርመር ይገባል፡፡የስር ፍርድ ቤትም ጉዳዩ ከዚህ አንጻር ተጣርቶ እንዲቀርብለት ለአዲስ አበባ ከተማ መሬት አስተዳደር ጠይቆ አስተዳደሩ በቁጥር አአ/መልአቢ/02/5613/14 በቀን 03/10/2014ዓ.ም ጽፎ በሰጠዉ ምላሽ ካርታ የተሰጠዉ 2ኛ ተጠሪ በቀን 07/12/2004 በቁጥር 458/059/04 በተጻፈ ደብደቤ በጠየቀዉ መሰረት ወጪ ሆኖ በቀን 08/12/2004ዓ.ም

ስለመሰጠቱ፤ይዞታዉ በ1988ም ጂ.አይ ኤስ ወይም 1997 መስመር ካርታ ላይ የማይታይ በመሆኑ ካርታዉ ሲዘጋጅ የቦታዉ ስፋት የተወሰነበት ሰነድ እና ይዞታዉን በምን አግባብ እንዳገኘች የሚያስረዳ ፋይላቸዉ ዉስጥ ማግኘት አለመቻሉን የገለጸ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ምስክሮችን ቃል ሰምቶ ካርታዉ የሚሰረዝበት ምክንያት የለም የሚል ድምዳሜ ላይ መድረሱን መዝገቡ ያሣያል፡፡

አመልካቾች አጥብቀዉ የተከራከሩት የስር ፍርድ ቤት መመሪያ ቁጥር 2/2004 ስር የተዘረዘሩት መስፈርቶች መሟላታቸዉን ሳያረጋግጥ ካርታ የተሰጠበት አግባብ ህጋዊ ነዉ በማለት የደረሰበት ድምዳሜ ስህተት ነዉ የሚል ነዉ፡፡ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረዉ በመመሪያ ቁጥር 2/2004 መሰረት ለእምነት ተቋማት በያዙት መሬት ላይ የይዞታ ማረጋገጫ የሚሰጥበበትን ዝርዝር መስፈርት አስቀምጧል፡፡አከራካሪዉን መሬት አስመልክቶ ይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠበት አግባብ የሚያሣይ ማስረጃ በማህደር ዉስጥ ማግኘት አለመቻሉን አስተዳደሩ ለፍርድ ቤቱ ገልጧል፡፡ከዚህ በኋላ ፍርድ ቤቱ ምስክሮችን ሰምቶ ተጠሪ ለመቃብር ሲትጠቀም የነበረ ቦታ ነዉ የሚለዉን በመቀበል ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡ይሁንና የቦታዉን አያያዝ የሚያስረዱ ሌሎች ሰነዶች ከሌሉ ቦታዉ ላይ ክርክር የሌለበት መሆኑ መጣራት አለበት፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ 1ኛ ተጠሪ ቦታዉን ከያዘች 27 ዓመት በላይ እንደሆነ የጠቀሰች ሲሆን አመልካቾች በበኩላቸዉ ቀደም ሲል አካባቢ ነዋሪ የሆኑት አዉራሻቸዉ እና ሌሎች ሰዎች ከይዞታቸዉ ላይ ቆርሰዉ በመስጠት እንዳቋቋሟት እና በካርታ ቁጥር 12/39/1/8/ 16444/28318/01 የተመዘገበዉ የ1ኛ ተጠሪ ይዞታ ላይ ክርክር እንደሌላቸዉ ነዉ፡፡አሁን ያከለራከረዉ ለመቃብር ተብሎ የተያዘዉ ቦታ ነዉ፡፡ይህ የመቃብር ቦታም በ1ኛ ተጠሪ ይዞታ ስር ነበር ለሚለዉ መከራከሪያ አመልካቾች አዉራሽ ጭምር በዚሁ ቦታ ላይ የተቀበሩ መሆኑን በመጥቀስ ነዉ፡፡ይሁንና ቦታዉ የመቃብር ብቻ ሳይሆን ሌሎችም አገልግሎቶች ጭምር የዋለ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ያሣያል፡፡ይህ ከሆነ ደግሞ የመቃብር ቦታ እና ለሌሎች አገልግሎት የዋለ ቦታ ምን ያህል እንደሆነ እና የተሻለ መብት ያለዉ ማነዉ የሚለዉ በግልጽ አልተጣራም፡፡

ስለዚህም በመመሪያ ቁጥር 2/2004 ለመቃብር ተብሎ በቦታዉ ላይ ለ1ኛ ተጠሪ ካርታ ሲሰራ በእርግጥም ክርክር የሌለበት ቦታ መሆን አለመሆኑን ፤ክርክር ያለበት እና የሌለበት ቦታ የትኛዉ እና መጠኑስ ምን ያህል ነዉ የሚል ተያያዥ የክርክር ጭብጥ በማስረጃ ማጣራት አለበት፡፡የስር ፍርድ ቤት ከዚህ አኳያ ግራቀኙ ማስረጃ እንዲያቀርቡ አድርጎ ማጣራት ሲገባዉ ካርታዉ የተሰራበትን ሁኔታ የሚያስረዱ ምስክሮችን የሰማ በተለይም ለዉሳኔ መሰረት ያደረገዉ 2ኛ ምስክር ሲሆን አመልካቾች በበኩላቸዉ ምስክሮቹ ሰነዱን ያዘጋጁ ባለሙያዎች በመሆናቸዉ ገለልተኛ አይደሉም የሚል መከራከሪያ ቀርቧል፡፡ ስለዚህም ክርክር የተነሳበት መሬት ላይ ተጠሪ ካርታ የተሰራበት አግባብ

በትክክልም ከክርክር ነጻ የነበረ መሆኑ ተረጋግጦ ነዉ ወይሥ አይደለም የሚለዉን በገለልተኛ ማስረጃ ማረጋገጥ ይገባል፡፡

ከዚህ ባሻገር ይህ ለክርክር ምክንያት የሆነዉ ካርታ እንዲሰረዝ በሌላ መዝገብ ተወስኗል በማለት አመልካቾች ያቀረቡትን መከራከሪያ አስመልክቶ 1ኛ ተጠሪ ሀሰት ነዉ፤አልመከነም በማለት ምላሽ ሰጥታለች፡፡ችሎቱም ጉዳዩን ለማጣራት አመልካቾች ከጠቀሱት ዉስጥ አንዱን መ/ቁ/ 181891 አስቀርቦ ተመልክቷል፡፡በመዝገቡ ላይ በይግባኝ አከራከሮ ዉሳኔ የሰጠዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሲሆን ያከራከረዉ ጉዳይ አሁን ክስ የቀረበበት ጋር ተመሳሳይ የሆነዉ ካርታ ቦሌ/3/53/2/4/16445/00 የሆነዉ የ1ኛ ተጠሪ ይዞታ ዉስጥ ስር ተከሳሽ ወ/ሮ አሰገደች ደገፋ ያለአግባብ 500ካ/ሜትር ቦታ ይዛለች በሚል 1ኛ ተጠሪ ባቀረበችዉ ክስ ተከሳሽ ቦታዉን ያገኘችዉ የልማት ተነሺ ምትክ ቦታ በከተማ አስተዳደር የተሰጠ ስለመሆኑ በማረጋገጥ ሊትለቅ አይገባም ተብሎ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠ ዉሳኔ ያጸና ሲሆን በተጨማሪም ቦታዉ ላይ የተሰጠዉ ካርታ መምከኑ ተጠቅሷል፡፡ይሁንና ካርታዉ ለምንና እንዴት እንደመከነ ወይም በሌላ አግባብ የተለወጠ ጉዳይ ስለመኖሩም ሆነ አሁን በተያዘዉ ክርክር ላይ የሚኖረዉ ህጋዊ ዉጤት በተመለከተ በስር ፍርድ ቤት ያልተጣራ ጉዳይ ስለሆነ በዚህ ሰበር ችሎት አቋም አልተወሰደበትም፡፡

ክርክሩ ተጠቃሎ ሲታይ ክርክር የተሳነበት ካርታ ቁጥር ቁጥር ቦሌ/3/53/2/4/16445/00 ለ1ኛ ተጠሪ የተሰጠበት እና መሬቱ የተያዘበት አግባብ ህጋዊነት ላይ የተነሳዉን ክርክር በመመሪያ ቁጥር 2/2004 አንቀጽ (1-5) ከተደነገገዉ መስፈረት አኳያ የሚያስረዳ የሰነድ ማስረጃ ማህደር ዉስጥ አለመኖሩ በስር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ይሁንና ካርታዉ ሲሰራ ቦታዉ ከይገባኛል ነጻ መሆን አለመሆኑ እና በቦታዉ ላይ መብት አለን የሚሉት አመልካቾች ጥያቄ ተገቢነት ያለዉ መሆን አለመሆኑ በስርዓት ተጣርቶ የተወሰደ ስለመሆኑ እንዲሁም ከሰነዱ ህጋዊነት ጋር ተያይዞ የተነሳዉን ክርክር እና ለመቃብር እና ሌሎች አገልግሎቶች የተያዘዉ መሬት መጠን ጋር በተያያዘም ተገቢዉን ማጣራት ሳይደረግ መወሰኑ የክርክር አመራር ስርዓት ጉድለት ያለበት መሆኑን ያሣያል፡፡የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰጠዉ ገዥ ዉሳኔ ለጉዳዩ አወሳሰን ተገቢዉ ጭብጥ ተይዞ ሳይጣራ የሚሰጥ ዉሳኔ የክርክር አመራር ስህተት መሆኑን እና በዚህ አግባብ የሚደርስ ድምዳሜ ተቀባይነት እንደሌለዉ እና በሰበር ችሎት ሊታረም የሚገባ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ስለመሆኑ በተለያዩ መዝገቦች ገዥ ዉሳኔ የሰጠበት ጉዳይ ነዉ፡፡(ሰበር መ/ቁ/43845፤ 37105 እና ሌሎች መዝገቦችን ይመለከቷል)፡፡

ሲጠቃለል ለክርክር ምክንያት የሆነዉ መሬት በ1ኛ ተጠሪ የተያዘበት አግባብ እና ካርታዉ የተሰራበት አግባብ ህጋዊ ስርዓትን ተከትሎ መሆን አለመሆኑ? 1ኛ ተጠሪ መሬቱን ለአመልካቾች ሊትለቅ ይገባል ወይስ አይገባም? ሊትለቅ ይገባል ከተባለስ ምን ያህል ነዉ ያለአግባብ የተወሰደባቸዉ? የሚሉትን ነጥቦች ከመመሪያ ቁጥር 2/2004 አንጻር ግራቀኙ በሚያቀርቡት ማስረጃ እና ገለልተኛ ምስክሮች በማስቀረብ እና

ጉዳዩ የሚመለከታቸዉ አስተዳደር አካላት ማብራሪያ በመጠየቅ ህጋዊ ዉጤቱ ሊወሰን ይገባል ብለናል፡፡ስለሆነም በጭብጥ አያያዝም ሆነ በተገቢዉ ማስረጃ በማጣራት ረገድ ስለክርክር አመራር ሰበር ችሎቱ የሰጠዉን ገዥ ዉሳኔ የሚቃረን ሆኖ ስላገኘን በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሸ) እና 10(1/ሐ) መሰረት በማረም ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1ኛ/በዚህ ጉዳይ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ131415 ላይ በቀን 30/03/2015ዓ.ም የሰጠዉ ፍርድ እና ይህንኑ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/302527 ላይ በቀን 23/05/2015ዓ.ም የተሰጠዉ ብይን በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስነስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2ኛ/የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መዝገቡን በማንቀሳቀስ ከላይ በፍርድ ሀተታ ላይ በተጠቀሱት እና ሌሎች አግባብነት ያላቸዉ ጭብጦች ዙሪያ ግራቀኙን በማከራከርና በማጣራት ተገቢዉን ዉሳኔ እንዲሰጥበት በማለት በሰበር ስነስርዓት አንቀጽ 9(2) መሰረት መዝገቡን መልሰንለታል፡፡ይጻፍ

3ኛ/በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መ/ቁ 131415 በመጣበት ሁኔታ ይመለስ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸምዓላማ አያገለግልም!

የሰበር መ/ቁ247851

ጥር 30 ቀን 2017

ዳኞች፡ ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ብርቅነሽ እሱባለው

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ

ተጠሪ፡ ታደሰ ከበበ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ ጠበቃ አስራት ከበደ ቀርቧል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ የግንባታ ውልን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረበው ክስ ነው፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው ተጠሪ ባቀረበው ክስ የጀሞ ጤና ጣቢያ ጂ + 5 ህንጻ ለማስራት ከአመልካች ጋር ግንቦት 29 ቀን 2009 ዓ.ም ውል የገባን ቢሆንም አመልካች በውሉ መሰረት የተሟላ ዲዛይን እና የግንባታ ፍቃድ በወቅቱ ባለመስጠቱ እንዲሁም ግንባታ የሚከናወንበትን ቦታ አጽድቶ ባለማስረከቡ ምክንያት ስራው በመጓተቱ በአመልካች ጥፋት ውሉ

ሰኔ 03 ቀን 2011ዓ.ም ተቋረጧል፡፡ በመሆኑም በሳይት ላይ ለተቀጠሩ ሰራተኞች ሳይሰሩ የተከፈላቸው ደመወዝ የኮንስትራክሽን ማሽን ስራ የፈቱበት ኪሳራ ግንባታው በመዘግየቱ ምክንያት የተፈጠረ ኦቨር ሄድ ወጪ ስራው እስከ መጨረሻው ቢሰራ ኖሮ ከስራው የሚገኘው ትርፍ የተሰራ ስራ በባለሞያ የተረጋገጠ ግምት በግንባታ ቦታ የገባው የግንባታ ማቴሪያል ግምት ላይ ለከሳሽ ቅድሚያ የተከፈለው ተቀንሶ ልዩነቱን በድምሩ 25,201,775.23(ሃያ አምስት ሚሊዮን ሁለት መቶ አንድ ሺህ ሰባት መቶ ሰባ አምስት ብር ከ23/100) ከወለድ ጋር እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡

አመልካች በሰጠው መልስ ጉዳዩ አይመለከተኝም የከተማ አስተዳደሩን አስፈፃሚ አካላት እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 64/2011 አንቀጽ 22(11) መሰረት የህንፃ ግንባታ ውልን የማስተዳደር የመፈፀም ሲጠናቀቅም በውሉ መሰረት መከናወናቸውን ተቆጣጥሮ መረከብ ኃላፊነት ያለበት የአዲስ አበባ ኮንስትራክሽን ቢሮ በመሆኑ ከክሱ በነፃ ልሰናበት ካልሆነው ወደ ክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ይደረግልኝ በማለት የመቃወሚያ ክርክር አቅርቧል፡፡ ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተም የግንባታው መዘግየት ሊመጣ የቻለው በዲዛይን ችግር እና የአፈር ምርመራ ውጤት በመዘግየቱ ሲሆን በዚህም ምክንያት ውል እንዲራዘም ተጠይቆ ውሉም የተራዘመ በመሆኑ ስራው የዘገየው በአመልካች ጥፋት አይደለም ለውሉ መዘግየት ተጠሪውም አስተዋጽኦ ያደረገ በመሆኑ ተጠያቂ ሊሆን አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡

የአዲስ አበባ ኮንስትራክሽን ቢሮ ጣልቃ እንዲገባ ተደርጎ አዋጅ ቁጥር 64/2011 ከመውጣቱ በፊት የነበሩ ግንባታዎችን የማስተዳደር ኃላፊነት ያልነበረብኝ በመሆኑ ልከሰስ አይገባም የሚል መቃወሚያ አቅርቦ በፍሬ ጉዳዩ ላይ በሰጠው መልስ ሚናየ ማማከር ብቻ ነው አመልካች የግንባታው ባለቤት በመሆኑ የግንቦታ ቦታውን ነጻ የማድረግ ካርታ የመያዝ የግንባታ ፈቃድ ማውጣት ኃላፊነቱን ባለመወጣቱ ለግንባታው መዘግየት ምክንያት ሆኗል በሌላ በኩል በጤና ሚ/ር በኩል ተዘጋጅቶ የቀረበው ዲዛይን ከቦታው ጋር የማይጣጣም በመሆኑ የዲዛይን ክላሳ መደረጉ እንዲሁም ተጠሪ የቁፋሮ ስራ የጀመረው በክረምት ወቅት በመሆኑ በዚህ ወቅት ስራ መስራት ባለመቻሉ ምክንያት ግንባታው ዘግይቷል፡፡ እነዚህ ምክንያቶች ከሳሽና ተከሳሽ ባደረጉት ውል አንቀጽ 44.1 መሰረት ካሳ የሚያስጠይቁ ስለመሆናቸው ያልተደነገገ በመሆኑ የተጠሪ የካሳ ይከፈለኝ ጥያቄ የህግም ሆነ የውል መሰረት የለውም፡፡ ለሰራተኛ የተከፈለ የተባለ የተሰራ ስስራ በሌለበት ኢቨር ሄድ ኮስት (ስራ ማስኬጃ) ተብሎ ክፍያ መጠየቁ እንዲሁም የታጣ ትርፍ በሚል

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

የቀረበው ጥያቄ ያላግባብ ለመበልፀግ ታስቦ የቀረበ ጥያቄ በመሆኑ ተገቢነት የለውም እንዲሁም በግንባታ ስፍራው ላይ የሚገኝ ምንም አይነት የግንባታ ግብዓት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

በሌላም በኩል ጣልቃ ገቡ የተከሳሽ ከሳሽነት በሚል የአሁን ተጠሪ  የቅድሚያ ክፍያ እና የመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትና እንዲያሳድስ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ከወሰደው ቅድሚያ ክፍያ ውስጥ ለሰራው ስራ ብር 1,002,000.00 ስራ ተቀናሽ ተደርጎ  ያልመለሰው እና የሚቀርበትን ብር 8,684,801.01 ከወለድ ጋር እንዲከፈል እንዲወሰን ጠይቋል፡፡ ተጠሪ በሰጠው መልስ ጣ/ገብ የራሱን ግዴታ ባልተወጣበት ሁኔታ እና ውሉ ወለድ የመጠየቅ መብት ሳይሰጠው ገንዘቡ ከነወለዱ እንዲከፈለው መጠየቁ ተገቢነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ በዚኅ መልኩ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ  ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ እና  በንብረት አቻ ግምታና  የማማከር ስራዎች ተጣርቶ እንዲቀርብ ካደረገ በኋላ በሰጠው ውሳኔ ተጠሪ ለማካካሻነት በተሰጠው ተጨማሪ ጊዜ ውስጥ ስራውን ማሰራት ከጀመረ በኋላ በአመልካች በኩል የግንባታ ፍቃድና የይዞታ ባለቤትነት ካርታና ፕላን ለተጠሪ ባለመስጠቱ እንዲሁም ቦታው ሶስተኛ አካል ነፃ በማድረግ የወሰን ስራ ባለመስራቱ ያገባኛል የሚል ሶስተኛ ወገን የተጠሪ ሰራተኞችን ከሳይቱ ቦታ በማባረሩ የስራ ውሉን ተጠሪ ያቋረጠው በአመልካች ጥፋት ነው፡፡ ጣልቃ ገቡን በሚመለከት የውሉ አካል ያልነበረ በመሆኑ ኃላፊነት የለበትም፡፡ ውሉ በአመልካች  ጥፋት በመቋረጡ በተጠሪ ላይ የደረሰው ኪሳራ ብር 22,711,014.11 በግንባታ ቦታ የቀረ የግንባታ ማቴሪያል ዋጋው ብር 114,080.00 እና ተጠሪ ሰራውን ሰርቶ ቢያጠናቀቅ ኖሮ የሚያገኘው ትርፍ ብር 4,044,090.99 ተደምሮ በጠቅላላ ብር 26,869,185.10 ኪሳራ እንደደረሰበት ሪፓርት ያቀረበ ቢሆንም ተጠሪ ዳኝነት የጠየቀው ብር 25,201,775.23 (ሀያ አምስት ሚሊዮን ሁለት መቶ አንድ ሺህ ሰባት መቶ ሰባ አምስት ብር ከሀያ ሶስት ሳንቲም) እንዲከፈለው በመሆኑ ይህንኑ ገንዘብ አመልካች ከህጋዊ ወለድ ጋር አመልካች ሊከፍለው  ይገባል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝቶ  ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት  ያቀረበ  ሲሆን አመልካች ለውሉ መቋረጥ ኃላፊነት አለበት ተብሎ ተጠሪ የጠየቀውን ገንዘብ ሊከፍል ይገባል በማለት የስር ፍርድ ቤት የደረሰበትን መደምደሚያ እና ተያያዥ ነጥቦችን ለማጣራት በሚል ጉዳዩን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በሰጠው ውሳኔ ለግንባታ ውሉ መቋረጥ አመልካች ኃላፊ አለመሆኑን በግልጽ በመካድ ያቀረበው ክርክር የለም የስር ፍርድ ቤት አመልካች የተሟላ ዲዛይን እና የግንባታ ፈቃድ በጊዜ ባለማቅረቡ ለውሉ መቋረጥ ምክንያት በመሆኑ

ኃላፊነቱንም መውሰድ አለበት ማለቱ እንዲሁም ተጠሪ የጠየቀውን የገንዘብ ክፍያም ጉዳዩን በገለልተኛ የንብረት ግመታና የማማከር ስራዎች በድጋሚ ተጣርቶ እንዲቀርብ በማድረግ ዳኝነት በተጠየቀበት ልክ እንዲከፈል መወሰኑ በአግባቡ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤት ያሳለፈውን ውሳኔ አፅንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ግንቦት 23/2015ዓ.ም ባቀረበው ማመልከቻ በውሳኔው ተፈፀመ የሚለውን የህግ ስህተት በመዘርዘር ስራው የዘገየው በዲዛይን ችግር እና የአፈር ምርመራ ውጤት ምክንያት መሆኑን እያወቀ ተጠሪ አመልካች ላይ ወጪ እንዳይጨምር ጉዳት ለመቀነስ የራሱ አስተዋጽኦ ያላደረገ በመሆኑ ለደረሰው ችግር የተጠሪ አስተዋፆ አለው በማለት ያቀረብነው ክርክር የስር ፍርድ ቤት አልፎ የሰጠው ውሳኔ ስህተት ነው የዲዛይን ችግር መኖሩና የአፈር ምርመራ ውጤት አለመምጣቱን ተጠሪ እያወቀ የግንባታ እቃ በሳይት ላይ አሳስቀመጠም እንጂ አስገብቷል ቢባል እንኳን አመልካችን ለኪሳራ ለማድረግ በማሰበብ የፈፀመው ድርጊት በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሮ አመልካች ኃላፊነት የለበትም ተብሎ ይወሰንልን የሚል ነው፡፡

ቅሬታው ተመርምሮ ኪሳራ እንዲከፈል የሚወሰነው አንደኛው ወገን ተዋዋይ ግዴታውን ባለመፈፀሙ ምክንያት በሌላኛው ተዋዋይ ወገን ላይ ጉዳት ደርሶበት እንደሆነ ስለመሆኑ የኪሳራው ልክም በደረሰው ጉዳት ልክ እንደሚሆንና ውሉ ባለመፈፀሙ ኪሳራ ደርሶብኛል የሚለው ወገን ኪሳራውን ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ መቀነስ ያለበት ስለመሆኑ ከፍ/ህ/ቁ1771(2)፣ 1802(1)፣ 2090 እና 2091 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም በተያዘው ጉዳይ አመልካች የሚጠበቅበትን ግዴታ ስለመፈፀሙ ተጠሪ የውል መራዙን አምኖ መቀበሉ ለጉዳቱ አስተዋጾ ማድረጉን ተጠሪ የዲዛይን ችግር ያለ መሆኑን እና የአፈር ምርመራ ውጤትም የዘገየ መሆኑን እያወቀ ጉዳቱ እንዳይቀጥል የራሱን ድርሻ ያልተወጣ እና ለጉዳቱም የራሱ አስተዋፆ አለበት በማለት ገልፀን ያቀረብነው መከራከርያ በስር ፍርድ ቤት መታለፉ የህግ ስህተት ነው በሚል የቀረበውን ቅሬታ አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪ ጥር 05 ቀን 2016ዓ.ም በሰጠው መልስ ከአመልካች ጋር የተፈፀመው ውል አመልካች የውል ጊዜውን ማራዘሚያ የካሳ ክፍያ ለተጠሪ የመክፈል ግዴታ እንዳለበት ይደነግጋል አመልካች ዲዛይኑን በወቅቱ ባለማስረከቡ የግንባታ ፍቃድ ባለማቅረቡ የወሰን ማስከበር ባለማስከበሩ ምክንያት ውሉ ሊራዘም በመቻሉ ተጠሪ የደረሰበት ኪሳራ እንዲከፍል መወሰኑ በአግባቡ ነው፡፡ አመልካች

ማሳ ታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ሳይፈቅድ ማሽነሪዎችና የሰው ኃይል ተጠሪ ማስወጣት ስለማይችል ለሚደርሰው ኪሳራ ውሉ ላይ አመልካች ተጠያቂ እንደሆነ ደንግጎ እያለ ኪሳራ የመቀነስ ግዴታ ተጠሪ አለው ተብሎ ውሉን ያላገናዘበ አቋም የተያዘበት ሁኔታ ስህተት ነው፡፡ ኪሳራ የመቀነስ ግዴታ ተጠሪ አልተወጣም በማለት ያቀረበው ቅሬታ በስር ፍርድ ቤት ያልተነሳ አዲስ ክርክር ስለሆነ አመልካች ያቀረበው ቅሬታ የህግ መሰረት የለውም ተብሎ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንዲፀና በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም ክርክሩን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርባል፡፡

ከፍ ሲል ባጭሩ የገለፅነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን ለችሎቱ የተያዘውን ጭብጥ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደሚቻለው ተጠሪ ለዚህ ሰበር ክርክር ምክንያት የሆነውን ዳኝነት የጠየቀው አመልካች በውሉ መሰረት የተሟላ ዲዛይን እና የግንባታ ፍቃድ በወቅቱ ባለመስጠቱ እንዲሁም ግንባታ የሚከናወንበትን ቦታ አጽድቶ ባለማስረከቡ ምክንያት ስራው በመጓተቱ በአመልካች ጥፋት ውሉ ስለተቋረጠ ለሰራተኞች ሳይሰሩ የተከፈላቸው ደመወዝ የማሽን ኪሳራ ኦቨር ሄድ ወጪ የሚገኘው ትርፍ ለተሰራ ስራና የግንባታ ማቴሪያል ግምት እንዲከፈለው እንዲወሰን ነው፡፡

አመልካች ለውሉ መቋረጥ ኃላፊነት እንደሌለበት ጠቅሶ የተከራከረ ቢሆንም ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለውሉ መቋረጥ ኃላፊነቱ የተጠሪ መሆኑ ተረጋግጧል በሚል ዳኝነት የተጠየቀበትን ገንዘብ እንዲከፍል የወሰነ ሲሆን ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም በኃላፊነትም ሆነ በመጠን ረገድ የተሰጠውን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

በበኩላችን እንደተመለከትነው አመልካች በኪሳራው ላይ ዝርዝር ቅሬታ አቅርቦ በቅሬታው መጨረሻ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ አመልካች ኃላፊነት የለበትም ተብሎ እንዲወሰን ቢጠይቅም በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው ውል የተቋረጠው በማን ጥፋት ነው? የሚለውን በተመለከተ የስር ፍርድ ቤት ፍሬ ነገሩን ለማጣራት እና ማስረጃ ለመመዘን በህግ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ክርክር እና የማስረጃውን ይዘት በመመርመር እና በመመዘን በአመልካች በኩል ግንባታ ፍቃድና የይዞታ ባለቤትነት ካርታና ፕላን ለተጠሪ ባለመስጠቱ እንዲሁም ቦታው ሶስተኛ አካል ነፃ በማድረግ የወሰን ስራ አለማሰራቱን ሁሉ አረጋግጦ ውሉን ተጠሪ ያቋረጠው በአመልካች ጥፋት ነው ተብሎ የተደረሰበት መደምደሚያ የሚነቀፍበት የህግ ምክንያት የለም፡፡

ይህ ከሆነ ደግሞ ቀጥሎ ሊታይ የሚገባው እና ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት እንዲቀርብ በተደረገበት የቅሬታ ጭብጥ እንደተመለከተው ሊከፈል የሚገባውን የኪሳራ ልክ እና ተጠሪ በህግ የተጣለበትን ኪሳራ የመቀነስ ግዴታ መወጣት አለመወጣቱን የሚመለከት ነው፡፡

ኪሳራን በተመለከተ ከፍ ሲል እንደተገለፀው የስር ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ በጠቅላላ ብር 26,869,185.10 ኪሳራ እንደደረሰበት በገለልተኛው ገማች አካል ሪፓርት ያቀረበ ቢሆንም ተጠሪ ዳኝነት የጠየቀው ብር 25,201,775.23 (ሀያ አምስት ሚሊዮን ሁለት መቶ አንድ ሺህ ሰባት መቶ ሰባ አምስት ብር ከሀያ ሶስት ሳንቲም) እንዲከፈለው በመሆኑ ይህንኑ ገንዘብ አመልካች ከህጋዊ ወለድ ጋር አመልካች ሊከፍለው ይገባል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ይሁንና ኪሳራ እንዲከፈል የሚወሰነው አንደኛው ወገን ተዋዋይ ግዴታውን ባለመፈፀሙ ምክንያት በሌላኛው ተዋዋይ ወገን ላይ ጉዳት ደርሶበት እንደሆነ ስለመሆኑ የኪሳራው ልክም በደረሰው ጉዳት ልክ እንደሚሆንና ውል ባለመፈፀሙ ኪሳራ ደርሶብኛል የሚለው ወገን ኪሳራውን ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ መቀነስ ያለበት ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ህ/ቁ1771(2)፣ 1802(1)፣ 2090፣ 2091 እና ተያያዥ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህም ሌላ ስለካሳ ጥያቄ የቀረበውን ለመወሰን ከተከሳሽ ክርክር ባሻገር ጉዳዩን በተገቢው ማስረጃ ሁሉ አጣርቶ መወሰን እንደሚገባ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ83 ግልጽ ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ስለሆነም በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ኪሳራ የመቀነስ ግዴታውን በህጉና በውሉ በአግባብ መወጣት አለመወጣቱ እንዲሁም የኪሳራው ልክ በደረሰው ጉዳት ልክ እንዲሆን ለማድረግ በአግባቡ ተጣርቶ ከፍሲል የተጠቀሱትን የህጉን ግልጽ ድንጋጌዎች እና መርሆች መሰረት ባደረገ መልኩ የኪሳራው ልክ ውሳኔ ሊሰጥበት ሲገባ በዚህ አግባብ ታይቶ አለመወሰኑን ተረድተናል፡፡ መሰል ፍሬ ነገር ተገቢው ትጋት ተደርጎበት በማስረጃ በአግባቡ እንዲጣራ ሳይደረግ የሚሰጥ ውሳኔ ህጋዊ መሰረት ያለው ነው ሊባል የሚችል ባለመሆኑ ውሳኔው የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

**ውሳኔ**

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 258529 ጥቅምት 4 ቀን 2014ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 216113 ሚያዝያ 30 ቀን 2015ዓ.ም ያሳለፈው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ348/1/ መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2. ውሉ የተቋረጠው በአመልካች ጥፋት ነው ተብሎ የተደረሰበት መደምደሚያ የሚነቀፍበት የህግ ምክንያት ባለመኖሩ ፀንቷል፡፡
3. ቀረበ የተባለውን ሪፓርት ብቻ መሰረት በማድረግ ተጠሪ የጠየቀው ብር 25,201,775.23 (ሀያ አምስት ሚሊዮን ሁለት መቶ አንድ ሺህ ሰባት መቶ ሰባ አምስት ብር ከሀያ ሶስት ሳንቲም) ከህጋዊ ወለድ ጋር አመልካች ሊከፍለው ይገባል በማለት የተሰጠው ውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
4. የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ ግራ ቀኙ ኪሳራ የመቀነስ ግዴታቸውን በህጉና በውሉ በአግባብ መወጣት አለመወጣታቸውን እና የሚያስከትለውን ውጤት እንዲሁም ኪሳራው በደረሰው ጉዳት ልክ እንዲሆን ለማድረግ ከክርክሩ የሚነሱ ሌሎች ተያያዥ ነጥቦችን በግራ ቀኙ ማስረጃ እና ተገቢነት ካለው ማስረጃ ሁሉ በማጣራቱ እንዲወስን ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ343/1/ መሰረት መልስናል፡፡ የውሳኔው ግልባጭ ይደረሰው፡፡
5. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት


የሰ/መ/ቁ 249367

*ጥር 28 ቀን 2017 ዓ/ም*

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ
ሽመክት አሰፋ
በእዉቀት በላይ
ማርታ ተካ
አየለ ማሞ

አመልካቾች፡- 1. ወ/ሮ ጌጤ ሙለታ
2. አቶ ሀብታሙ ሙለታ
3. አቶ አበራ ሙለታ
} - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ብርሃኔ ካባ - የቀረበ የለም

መዝገቡ የተቀጠረዉ የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ ተገቢዉን ለመስራት ሲሆን ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍርድ</u>

ይህ የሰበር መዝገብ ተከፍቶ ለዚህ ሰበር ችሎት የቀረበዉ የአምቦ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 81891 በ13/03/2015 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉና የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 52751 በ07/04/2015 ዓ/ም፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ችሎት በመ/ቁጥር 411634 በ23/05/2015 ዓ/ም እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 422273 በ20/07/2015 ዓ/ም በዋሉ ችሎቶች በትዕዛዝ ያጸኑት የሰጡት ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን ገልጸዉ አመልካቾች በ16/10/2015 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸዉ ነዉ፡፡


<u>ማስታወሻ</u>፡ - ይህ የሰበር ችሎት ዉሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ለዚህ የሰበር አቤቱታ መቅረብ ምክንያት የሆነዉ ጉዳይ የዉርስ ክርክርን የሚመለከት ሆኖ ክርክሩ የተጀመረዉ በአምቦ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን በወረዳዉ ፍርድ ቤት አመልካቾች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾች በአምቦ ወረዳ ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ሟች አባታቸዉን ሙለታ ካባን ተክተዉ ከሟች አያቶቻቸዉ አቶ ካባ ዳባ እና ወ/ሮ ብርቱካን ፈካንሳ በዉርስ ሊያገኟቸዉ የሚገቡ በአምቦ ወረዳ ኢላሙ ጎርሚቲ ቀ/ገ/ማኅበር ዉስጥ በስድስት በተለያዩ ቦታዎች የሚገኙትን የገጠር እርሻ ይዞታዎችን፣ በይዞታዎቹ ላይ የተፈሩ ቋሚ ሀብቶችንና የተለያዩ ከብቶችን ተጠሪ ከድርሻቸዉ በላይ ይዘዉ የሚገኙ መሆናቸዉን ገልፀዉ የዉርስ ሀብቶቹ ተጣርተዉ የሟች አባታቸዉን የዉርስ ድርሻ እንዲሁም ከፊሎቹ ከሳሾች ራሳቸዉን ችለዉ በጥገኝነት ሊያገኙ የሚገባቸዉን የዉርስ ድርሻ እንዲያገኙ እንዲወሰንላቸዉ ዳኝነት በመጠየቅ ክስ አቅርበዋል፡፡

ለዚህ የአመልካቾች ክስ መልስ እንዲሰጡ የታዘዙት ተጠሪ በበኩላቸዉ በአመልካቾች የክስ ማመልከቻ ላይ ከተጠቀሱ ስድስት ይዞታዎች መካከል በተራ ቁጥር አንድና አምስት ላይ የተጠቀሱት ሁለቱ ይዞታዎች ሟቾቹ በሕይወት እያሉ ለተጠሪ በስጦታ ሰጥተዉ ከ2001 ዓ/ም ጀምሮ በተጠሪ ስም ተመዝግበዉ የገጠር መሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ጭምር ተሰጥቷቸዉ በግላቸዉ እየተጠቀሙ ያሉ መሆኑን፣ በእነዚህ ሁለት ይዞታዎች ላይ ያሉ ቋሚ አታክልትና ቤትም የተጠሪ እንጂ የሟቾች ሀብቶች አለመሆናቸዉን፣ በክሱ በተራ ቁጥር ስድስት ላይ የተጠቀሰዉ ይዞታ ደግሞ በእጃቸዉ የሌለና ሌላ ሰዉ ይዞት የሚገኝ መሆኑን እና ከብቶቹ ሟቾች በሕይወት በነበሩ ጊዜ ሽጠዉ የተጠቀሟቸዉና የሌሉ መሆኑን ገልጸዉ የተከራከሩ ሲሆን የግራ ቀኙን ክርክር የመረመረዉ የወረዳዉ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 81891 በ29/04/2014 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት በክሱ ከተጠቀሱ ይዞታዎች መካል ሁለቱ ለተጠሪ በስጦታ የተሰጡ መሆናቸዉንና አንደኛዉ ይዞታ ደግሞ በሌላ ሦስተኛ ወገን እጅ ያለ መሆኑን እንዲሁም ሟቾች ሲሞቱ ከብቶቹ ስለመኖራቸዉ አመልካቾች አለማስረዳታቸዉን ገልጾ ክሱን ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

አመልካቾች በዚህ የአምቦ ወረዳ ፍርድ ቤት ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ይግባኝ ሰሚዉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 51733 ግራ ቀኙን አከራክሮ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ ለተጠሪ በስጦታ ተላልፈዋል የተባሉ ሁለት ይዞታዎችንና በሌላ ሦስተኛ ወገን እጅ ይገኛል የተባለዉን ይዞታ እንዲሁም የቤት እንስሳትን አስመልክቶ የወረዳዉ ፍ/ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ አጽንቶ ነገር ግን በክሱ ላይ የተጠቀሱ ሌሎች ሦስት ይዞታዎችን በተመለከተ ምንም ዓይነት ማጣራት ሳይደረግ መታለፉ አግባብ አለመሆኑን ተችቶ የወረዳዉ ፍ/ቤት እነዚህ ሦስት ይዞታዎች መኖር አለመኖራቸዉንና የሟቾች ወራሾችም እነ ማን እንደሆኑ ለይቶ ተጠሪ በዉርስ ክፍፍሉ ለመሳተፍ የሚፈልጉ ከሆነ አስቀድሞ በስጦታ የተቀበሏቸዉን ይዞታዎችን በፍ/ሕ/ቁጥር 1065 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሠረት ወደ ዉርሱ እንዲመልሱ በማድረግ ክፍፍሉ እንዲፈጸም እንዲወስን በመግለጽ ጉዳዩን ወደ ወረዳዉ ፍ/ቤት መልሶታል፡፡

ከዚህ በኋላ አስቀድሞ በዉሳኔ የዘጋዉን መዝገብ ዳግም ያንቀሳቀሰዉ የወረዳዉ ፍ/ቤት በአመልካቾች የክስ ማመልከቻ በተራ ቁጥር 2 እስከ አራት ከተጠቀሱ ሦስት ይዞታዎች መካከል ሁለቱ በ2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች እጅ እንደሚገኙና በተራ ቁጥር 4 ላይ የተጠቀሰዉ ይዞታ ደግሞ በተጠሪ እጅ እንዳለ እንዲሁም የሟቾች ወራሾች የአመልካቾችን አባትንና ተጠሪን ጨምሮ አራት ስለመሆናቸዉ በማስረጃ መረጋገጡን ገልጾ በአመልካቾች እጅ የሚገኙ ሁለት

ይዞታዎችንና ለተጠሪ በስጦታ ያልተሰጣቸዉ ሆኖ በእጃቸዉ ላይ ያለዉን አንድ ይዞታ አራቱ የሟቾች ወራሾች እንዲካፈሉና አመልካቾች አባታቸዉን ተክተዉ ከእነዚህ ሦስት ይዞታዎች ላይ 1/4ኛ ድርሻቸዉን እንዲወስዱ ገልጾ በ13/03/2015 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት የወሰነ ሲሆን በዚህ ዉሳኔ ላይ ይግባኝ ያቀረበላቸዉ የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እንደ ቀደም ተከተላቸዉ በመ/ቁጥር52751 በ07/04/2015 ዓ/ም እና በመ/ቁጥር 411634 በ23/05/2015 ዓ/ም እንዲሁም የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 422273 በ20/07/2015 ዓ/ም በዋሉ ችሎቶች በሰጡት ትዕዛዝ ይግባኙንና የሰበር አቤቱታዉን ሰርዘዋል፡፡

በመሆኑም አመልካቾች ይህ የአምቦ ወረዳ ፍርድ ቤት ዉሳኔና ከምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እስከ ኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ድረስ በየደረጃዉ ያሉ የክልሉ ፍ/ቤቶች ዉሳኔዉን በማጽናት የሰጡት ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስለመሆኑ በአቤቱታቸዉ ላይ ያነሱት ዋና የቅሬታ ነጥብ ተጠሪ በዉርሱ ተካፋይ ለመሆን የሚፈልጉ ከሆነ አስቀድሞ በስጦታ የተቀበሏቸዉን ንብረቶችን (ይዞታዎችን) ወደ ዉርሱ ሀብት ተመላሽ እንዲያደርጉ አሊያም ከዉርሱ ዉጭ እንዲሆኑ ሳይደረግ በስጦታ የተቀበሏቸዉን ንብረቶችን ለብቻቸዉ እንደያዙ የዉርሱ ተካፋይ ሆነዉ ቀሪ የዉርስ ንብረቶችን ከሌሎች ወራሾች ጋር እንዲካፈሉ መደረጉ የፍ/ሕ/ቁጥር 1065 እና ተከታዮቹን ድንጋጌዎችን የሚቃረን መሆኑን የሚገልጽ ነዉ፡፡

ይህ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ተመርምሮ ተጠሪ አስቀድሞ በስጦታ የተቀበሏቸዉን ይዞታዎችን እንደያዙ ቀሪ ይዞታዎችን ከሌሎች ወራሾች ጋር እኩል እንዲካፈሉ መወሰኑ ከፍ/ሕ/ቁጥር 1065 እስከ 1079 ድንጋጌዎችና በዚህ ረገድ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 113247፣ 160761 እና በሌሎችም መዝገቦች ከሰጣቸዉ አስገዳጅ ዉሳኔዎች አኳያ በሰበር ሊታይ የሚገባ መሆኑን ገልጾ ተጠሪ ለአቤቱታዉ መልስ እንዲሰጡ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ በዚህም መሠረት ተጠሪ ቀርበዉ በ21/11/2016 ዓ/ም ጽፈዉ በሰጡት መልስ ሟቾች በሕይወት በነበሩ ጊዜ ለተጠሪ በስጦታ የሰጧቸዉ ይዞታዎች የሟቾች ሀብት ስላልሆኑ የዉርስ

ሀብት ክፍፍል ጥያቄ ሊቀርብባቸዉ እንደማይችል፣ የይዞታዎቹ ስጦታ ሟቾቹ በሕይወት እያሉ ተፈጻሚነትን አግኝቶ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በስማቸዉ ተሠርቶ መሰጠቱ ሟቾች ስጦታዉ የማይመለስ (የማይሻር) ስጦታ እንዲሆን መፍቀዳቸዉን ስለሚያመለክት እነዚህ ይዞታዎች ዳግም ወደ ዉርሱ ሀብት ሊመለሱ የሚችሉበት አግባብ አለመኖሩንና ስጦታዉ የማይመለስ ስጦታ መሆኑን ገልጾ የወረዳዉ ፍ/ቤት አስቀድሞ በ24/09/2014 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት ሰጥቶ የነበረዉን ዉሳኔ የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 51733 በ29/10/2014 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት በሰጠዉ ዉሳኔ ያጸና በመሆኑ አመልካቾች ይህንን የቀደመዉን የወረዳዉንና የከፍተኛዉን ፍ/ቤት ዉሳኔ በይግባኝ አስመርምረዉ ባላስለወጡበት ለተጠሪ በማይመለስ ስጦታ የተሰጡ ስለመሆናቸዉ በፍርድ ጭምር የተረጋገጡ ይዞታዎች ወደ ዉርሱ ሀብት እንዲመለሱ ሊጠይቁ የሚችሉበት የሕግ አግባብ እንደሌለ ገልጸዉ ሰፋ ያለ መልስ ሰጥተዋል፡፡ የሰበር አመልካቾችም የሰበር ቅሬታቸዉን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ አጠር ተደርጎ የተገለጸዉ ሲሆን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር አቤቱታዉ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ ከላይ እንደተገለጸዉ በአመልካቾች የክስ ማመልከቻ በተራ ቁጥር 1 እና 5 ላይ የተጠቀሱ ይዞታዎች ሟቾች በሕይወት በነበሩ ጊዜ ለተጠሪ በስጦታ ተሰጥተዉ ከ2001 ዓ/ም ጀምሮ በተጠሪ ስም ተመዝግበዉ የሚገኙ ስለመሆኑ የአምቦ ወረዳ ፍ/ቤት በ24/09/2014 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት እና የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 51733 በ29/10/2014 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት በሰጡት ዉሳኔ የተረጋገጠ ጉዳይ ነዉ፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ተጠሪ በቀሪዉ የዉርስ ሀብት ክፍፍል ላይ ተካፋይ ለመሆን ከፈለጉ በፍ/ሕ/ቁጥር 1065 እና 1066 ላይ በግልጽ በተደነገገዉ መሠረት አስቀድሞ በስጦታ የተቀበሏቸዉን ይዞታዎችን ወደ ዉርሱ የመመለስ ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡ ተጠሪ ከዚህ የመመለስ ግዴታ ነጻ ሊሆኑ የሚችሉት በፍ/ሕ/ቁጥር 1067(1) ላይ እንደተደነገገዉ ሟቾች ስጦታዉን ለተጠሪ ሲሰጧቸዉ ተጠሪ በስጦታ የተቀበሏቸዉን ይዞታዎችን ሳይመልሱ ቀሪዉን ዉርስ እንዲካፈሉ የፈቀዱ በሆነ ጊዜ ብቻ ሲሆን ይህንን የሟቾችን ሃሳብ ለማረጋገጥ ደግሞ ግልጽ የሆነ የዉል ቃል መኖሩ አስፈላጊ ስለመሆኑ በፍ/ሕ/ቁጥር 1067(2) ላይ በግልጽ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ተጠሪ ግን በዚህ ረገድ ይዞታዉ በስማቸዉ ተመዝግቦ መገኘቱ ስጦታዉ የማይሻር ስጦታ ስለመሆኑ እንደሚያመለክት ገልጸዉ ግምታቸዉን ብቻ መሠረት በማድረግ ከሚከራከሩ በቀር ስጦታዉ ሲሰጣቸዉ በማይሻር መልኩ የተሰጣቸዉ መሆኑን የሚያረጋግጥ ግልጽ የሆነ ዉል አላቀረቡም፡፡ እንዲሁም የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 51733 በ29/10/2014 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት በጉዳዩ ላይ ሲወስንም ሁለት ይዞታዎች ለተጠሪ በስጦታ የተሰጡ ስለመሆናቸዉ የወረዳዉ ፍ/ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ በማስረጃ የተደገፈ መሆኑን ብቻ ከመግለጹ በቀር እነዚህ ለተጠሪ በስጦታ የተሰጡ ይዞታዎች በማይመለስ አኳኋን የተሰጡ መሆናቸዉን ገልጾ የሰጠዉ ዉሳኔ የለም፡፡ ይልቁንም ከፍተኛዉ ፍ/ቤት በዚሁ ዉሳኔዉ ላይ «ከክፍፍል ሁኔታ ጋር በተያያዘ … መልስ ሰጭም (የአሁን ተጠሪ) ሆኑ ከይግባኝ ባዮች (የአሁን አመልካቾች) ዉስጥ የአዉራሾች መሬት በእጃቸዉ ያለዉ በፍ/ሕ/ቁጥር 1065 እና በተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሠረት በእጃቸዉ የያዙት በዉርሱ እንዲካተት ተደርጎ በዉርስ ሥርዓት መሠረት በመመለስ መከፋፈል አለበት፡፡»

በማለት ከተጠሪ ክርክር ተቃራኒ የሆነ ዉሳኔ መስጠቱን ከሰበር አቤቱታዉ ጋር ተያይዞ የቀረበዉ የከፍተኛዉ ፍ/ቤት ዉሳኔ ያመለክታል፡፡

ይህ ከሆነ ደግሞ ተጠሪ በቀሪዉ የዉርስ ሀብት ክፍፍል ላይ ለመሳተፍ የሚፈልጉ ከሆነ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 113247፣ 160761፣ 162475 እና በሌሎችም መዝገቦች በሰጣቸዉ አስገዳጅ ዉሳኔዎች መሠረት አስቀድሞ በስጦታ የተቀበሏቸዉን ሁለት ይዞታዎችን ወደ ዉርሱ ሀብት መመለስ አለበለዚያም ከቀሪዉ የዉርስ ሀብት ክፍፍል ዉጭ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ አስቀድሞ በስጦታ ያገኟቸዉን ይዞታዎችን እንደያዙ ቀሪዉን የዉርስ ሀብት ከሌሎች ወራሾች ጋር ለመከፋፈል እንደሚችሉ ገልጸዉ የሚያቀርቡት ክርክርም ሆነ የሥር ፍ/ቤቶች ይህንን ክርክራቸዉን ተቀብለዉ የሰጡት ዉሳኔ የፍ/ሕ/ቁጥር 1065-1067 ግልጽ ድንጋጌዎችንም ሆነ በዚህ ረገድ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከላይ በተጠቀሱና በሌሎችም መዝገቦች የሰጠዉን አስገዳጅ ዉሳኔ የሚቃረን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም ስህተቱ ታርሞተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ዉሳኔ</u>

1. የአምቦ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 81891 በ13/03/2015 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉና የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 52751 በ07/04/2015 ዓ/ም፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ችሎት በመ/ቁጥር 411634 በ23/05/2015 ዓ/ም እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 422273 በ20/07/2015 ዓ/ም በዋሉ ችሎቶች በትዕዛዝ ያጸኑት ዉሳኔ በፍ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 348(1) መሠረት ተሻሽሏል፡፡

2. ተጠሪ በሥር የክስ ማመልከቻ በተራ ቁጥር አንድ እና አምስት ላይ የተጠቀሱ ይዞታዎችን ከሟች ወላጆቻቸዉ በስጦታ ያገኙ ስለመሆኑ እንዲሁም ባለበት ሁኔታ የሟቾች የዉርስ ሀብት ሊሆኑ የሚችሉት በክስ ማመልከቻዉ ከተራ ቁጥር ሁለት እስከ አራት የተጠቀሱ ይዞታዎች እንደሆኑ ተገልጾ የተሰጠዉ የዉሳኔ ክፍል በፍ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡

3. ተጠሪ እነዚህን የዉርስ ሀብቶችን ለመካፈል የሚችሉት አስቀድሞ በስጦታ ያገኟቸዉን በክሱ በተራ ቁጥር አንድ እና አምስት ላይ የተጠቀሱትን ይዞታዎችን ወደ ዉርሱ ሲመልሱ ብቻ በመሆኑ እነዚህን ይዞታዎችን ሳይመልሱ ሌሎች የዉርስ ይዞታዎችን ከሌሎች ወራሾች ጋር እንዲካፈሉ ተገልጾ የተሰጠዉ የዉሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡

4. ተጠሪ አስቀድሞ ከሟች ወላጆቻቸዉ በስጦታ ያገኟቸዉን ሁለት ይዞታዎችን መልሰዉ ወደ ዉርሱ ሀብት ዉስጥ ለማስገባት ፈቃደኛ አለመሆናቸዉ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጠ በመሆኑ በዉርስ ክፍፍሉ ተካፋይ እንዳይሆኑ ተደርጎ ሦስቱን የዉርስ ይዞታዎችን ሌሎች የሟቾች ወራሾች ብቻ በሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ ላይ በተመለከተዉ የድርሻ መጠናቸዉ ልክ እንዲከፋፈሉ ተወስኗል፡፡
5. የዚህን ሰበር ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ በዉሳኔ ስለተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

<u>ማስታወሻ፡</u> - ይህ የሰበር ችሎት ዉሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

የሰ/መ/ቁ250349

ጥር 26 ቀን 2017 ዓ/ም

ዳኞች፡- ሽመክት አሰፋ

በእዉቀት በላይ

መላኩ ካሳዬ

ማርታ ተካ

አየለ ማሞ

አመልካች፡- አቶ መሐመድ አሊይ ገዳሊ ተወካይ ከድር መህመድ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ ቀቡላ አልይ ኡስማን

2. ወ/ሮ ቢፍቱ አልይ ኡስማን } ጠበቃ ኤባ በየነ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረዉ የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ ተገቢዉን ለመስራት ሲሆን ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ይህ የሰበር መዝገብ ተከፍቶ ለዚህ ሰበር ችሎት የቀረበዉ የምስራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 104148 በ14/06/2015 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ምስራቅ ኦሮሚያ ቋሚ ምድብ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 417271 በ20/07/2015 ዓ/ም እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 422813 በ03/09/2015 ዓ/ም በዋሉ ችሎቶች በትዕዛዝ ያጸኑት ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን ገልጸዉ አመልካች በ05/11/2015 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸዉ ነዉ፡፡

ለዚህ የሰበር ክርክር ምክንያት የሆነዉ ጉዳይ የተጀመረዉ በሐረማያ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን በወረዳዉ ፍርድ ቤት አመልካች ተከሳሽ ተጠሪዎች ደግሞ ከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪዎች

በሕይወት በነበሩ ጊዜ በ1998 ዓ/ም ለዚህ የሰበር ክርክር ምክንያት የሆኑትን ሁለት የገጠር እርሻ መሬት ይዞታዎችን እኩል እንዲያርስ ሰጥተዉት እስከ ዕለተ ሞታቸዉ ድረስ ምርቱን እኩል ሲጠቀሙ ቆይተዉ ከሞቱ በኋላ ወራሽነታቸዉን አረጋግጠዉ መብታቸዉን እንዲጠብቅላቸዉ ቢጠይቁትም ከልክሏቸዉ ለብቻዉ እየተጠቀመ ስለሚገኝ ይዞታዉን እንዲለቅላቸዉ በሀገር ሽማግሌዎች ቢያስጠይቁትም እንቢተኛ ሆኖ ስለተገኘ ከሁለቱ ይዞታዎች በአንደኛዉ ላይ ከፈቃዳቸዉ ዉጭ የሠራዉን ሰባት ክፍል ቤት በራሱ ወጪ አፍርሶ ይዞታዉን እንዲለቅ እንዲወሰንላቸዉ ዳኝነት በመጠየቅ ክስ አቅርበዋል፡፡

ለዚህ የተጠሪዎች ክስ መልስ እንዲሰጡ በፍ/ቤቱ የታዘዙት አመልካች በበኩላቸዉ ተጠሪዎች በክሳዉ ላይ የጠቀሱትን ይዞታ በ1983 ዓ/ም የተጠሪዎችን እህት ሲያገቡ የተጠሪዎች ወላጅ አባት የሰጧቸዉና ከዚያን ጊዜ ጀምሮም ተጠሪዎችን ጨምሮ ከማንም ሰዉ አንዳችም ተቃዉሞ ሳይቀርብባቸዉ በስማቸዉ አስመዝግበዉና ከብር 21,126,000 (ሃያ አንድ ሚሊየን አንድ መቶ ሃያ ስድስት ሺህ) በላይ ዋጋ ያለዉን ጫትና ከብር 9,000,000 (ዘጠኝ ሚሊየን) በላይ ዋጋ ያለዉን ባሕር ዛፍ ተክለዉበት እንዲሁም ተጠሪዎች በክሳቸዉ ላይ የጠቀሱትን ባለ ሰባት ክፍል የመኖሪያ ቤት ሠርተዉበት እየተጠቀሙ የሚገኙበት ይዞታ እንጂ ከተጠሪዎች አባት ለጋራ እርሻ የተሰጣቸዉ ይዞታ አለመሆኑን ገልጸዉ ክሱ ዉድቅ እንዲደረግ በመጠየቅ ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ በኋላ የወረዳዉ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ከሰማና ስለ ይዞታዉ ከወረዳዉ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት ጠይቆ ካረጋገጠ በኋላ አመልካች የክርክሩን ይዞታ በጋብቻ ምክንያት የተጠሪዎች አባት ሰጥተዋቸዉ ከ30 ዓመት በላይ ለሆነ ጊዜ በመያዝ ቤት ሠርተዉበትና ጫት ተክለዉበት ሲጠቀሙ የቆዩ ስለመሆኑ የአመልካች (የሥር ተከሳሽ) የመከላከያ ምስክሮች ከሰጡት ምስክርነት ባሻገር ከወረዳዉ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት በትዕዛዝ ተጠይቆ በቀረበዉ ሪፖርት ጭምር መረጋገጡንና ይዞታዉ ለአመልካች (ለሥር ተከሳሽ) የተሰጣቸዉ በእኩል እርሻ ስለመሆኑ የተጠሪዎች ምስክሮች በአሳማኝ ሁኔታ እንዳላስረዱ ገልጾ የተጠሪዎችን ክስ ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

ተጠሪዎች በዚህ የሐረማያ ወረዳ ፍርድ ቤት ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለምስራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ይግባኝ ሰሚዉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 104148 ይግባኙን መርምሮ ግራ ቀኙን ካከራከራቸዉ በኋላ በ14/06/2015 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት አመልካች የክርክሩን ይዞታ ለእኩል እርሻ የያዘ ስለመሆኑ በተጠሪዎች ማስረጃ እንደተረጋገጠ ገልጾ የወረዳዉን ፍ/ቤት ዉሳኔ በመሻር አመልካች በይዞታዉ ላይ የሠሩትን ቤት በራሳቸዉ ወጪ አንስተዉ ይዞታዉን ለተጠሪዎች እንዲለቁ የወሰነ ሲሆን ዉሳኔዉን በይግባኝና በሰበር የመረመሩት

በመሆኑም አመልካች ይህ የምስራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዉሳኔ እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ሰሚ ችሎት ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስለመሆኑ በአቤቱታቸዉ ላይ ያነሱት ዋና የቅሬታ ነጥብ አመልካች ማንም ሳይቃወማቸዉ የክርክሩን ይዞታ ለ30 ዓመታት ይዘዉ በስማቸዉ ግብር በመክፈልና የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ጭምር በማዉጣት በይዞታዉ ላይ ቋሚ አታክልትን በመትከልና የመኖሪያ ቤት በመሥራት ሲጠቀሙበት የቆዩ መሆናቸዉ ተረጋግጦ ባለበት ይዞታዉ የተጠሪዎች የዉርስ ይዞታ እንደሆነ ተገልጾ መወሰኑ የገጠር መሬት አጠቃቀም አዋጅን የጣሰ መሆኑን የሚገልጽ ነዉ፡፡

ይህ የአመልካች የሰበር አቤቱታ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ተመርምሮ አመልካች የክርክሩን ይዞታ ለ30 ዓመታት ይዘዉ ቤት ሠርተዉና ቋሚ ሀብት አፍርተዉበት ሲጠቀሙ መቆየታቸዉ በግራ ቀኙ ማስረጃ ጭምር ተረጋግጦ ባለበት ይዞታዉን የያዙት በእኩል አራሽነት እንደሆነ ተገልጾ እንዲለቁ የተወሰነበት አግባብ በሰበር ሊታይ የሚገባ መሆኑን ገልጾ ተጠሪዎች ለአቤቱታዉ መልስ እንዲሰጡ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

በዚህም መሠረት ተጠሪዎች ቀርበዉ በ16/03/2017 ዓ/ም በጠበቃቸዉ አማካይነት ጽፈዉ በሰጡት መልስ አመልካች በወረዳዉ ፍ/ቤት መልስ ሲያቀርብ የተከራከረዉ መሬቱን በ17,000 ብር መግዛቱን ገልጾ እንጂ ከሟች አባታቸዉ በስጦታ ማግኘቱን ገልጾ ባለመሆኑ በሰበር ደረጃ ያቀረበዉ አዲስ ክርክር ተቀባይነት እንደሌለዉ፣ የክርክሩ መሬት ለአመልካች የተሰጠዉ ለእኩል እርሻ ስለመሆኑ በተጠሪዎች ማስረጃ በሚገባ እንደተረጋገጠ እና የተጠሪዎች አባት ለአመልካች ያደረጉት እንዳችም ስጦታ ስለመኖሩ አመልካች በማስረጃ እንዳላስረዳ እና አመልካች የክርክሩን ይዞታ በስሙ ስለማስመዝገቡ በሥር ፍ/ቤቶች ያቀረበዉ ማስረጃም እንደሌለ ገልፀዉ የሰበር አቤቱታዉ የቀረበበት የምስራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ዉሳኔና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚና ሰበር ሰሚ ችሎቶች ዉሳኔዉን በማጽናት የሰጡት ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ሊባል የሚቻል ስላይደለ እንዲጸናላቸዉ በመጠየቅ መልስ ሰጥተዋል፡፡ የሰበር አመልካችም የሰበር ቅሬታቸዉን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ አጠር ተደርጎ የተገለጸ ሲሆን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር አቤቱታዉ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ ከላይ በአጭሩ እንደተገለጸዉ የክርክሩ ዋና ነጥብ አመልካች የክርክሩን ይዞታ ለአመልካቾች ሊለቁ የሚገባ መሆን አለመሆኑን የሚመለከት ነዉ፡፡ የሥር ሁሉም ፍ/ቤቶች ዉሳኔ በግልጽ እንደሚያመለክተዉ አመልካች በክርክሩ ይዞታ ላይ ቤት ሠርተዉና ጫት ተክለዉበት ለበርካታ ዓመታት የኖሩ ስለመሆኑ ከአመልካች ማስረጃ ባሻገር

ቤት ሠርተዉበት ይዞታዉን ይዘዉ የሚገኙ መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡ ግራ ቀኙ የሚለያዩበት ዋናዉ ነጥብ አመልካች ይዞታዉን የያዙት በእኩል እርሻ አሊያም በስጦታ ስለ መሆኑ ላይ ብቻ ነዉ፡፡ በዚህ ረገድ ተጠሪዎች ያቀረቧቸዉ ምስክሮች የክርክሩ ይዞታ የተጠሪዎች አባት እንደነበረ፣ አመልካች የተጠሪዎችን እህት ስላገቡ የተጠሪዎች አባት ይዞታዉን ለአመልካች እንደሰጡና የተጠሪዎች አባት ይዞታዉን ለአመልካች የሰጡት ለእኩል እርሻ ስለመሆኑ እንደሰሙ ገልፀዉ የመሰከሩ ሲሆን በአንጻሩ የአመልካች የመከላከያ ምስክሮች ደግሞ አመልካች ከደርግ ዘመን ጀምሮ ይዞታዉ ተሰጥቷቸዉ ቤት ሠርተዉና ጫት ተክለዉ ከልጆቻቸዉና ከሚስቶቻቸዉ ጋር ሲጠቀሙ እንደቆዩ ገልጸዉ ስለመመስከራቸዉ በሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ ላይ በግልጽ ተመልክቶ ይገኛል፡፡

እንግዲህ እነዚህን በሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ ላይ በግልጽ ተመዝግበዉ የሚገኙ ፍሬ ነገሮችን በመያዝ ክርክሩን ስንመረምረዉ በመጀመሪያ ደረጃ የተጠሪዎች ምስክሮች በአንድ በኩል አመልካች የተጠሪዎችን እህት ስላገቡ የተጠሪዎች አባት የክርክሩን ይዞታ ለአመልካች እንደሰጡና አመልካች በይዞታዉ ላይ ቤት ሠርተዉበት እንደሚኖሩ ሲመሰክሩ በሌላ በኩል የክርክሩ ይዞታ  ለእኩል እርሻ እንደተሰጣቸዉ እንደሰሙ ገልጸዉ መመስከራቸዉ እርስ በርሱ የሚቃረን ከመሆኑም ባሻገር ይዞታዉ ለአመልካች ለእኩል እርሻ ስለመሰጠቱ እንደሰሙ ከመግለጽ በቀር ይህንን ራሳቸዉ በቀጥታ የሚያዉቁ ስለመሆናቸዉ ያስረዱት ነገር የለም፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ አንድን ይዞታ ለእኩል እርሻ የሚይዝ ሰዉ ይዞታዉን አርሶ ብቻ ከሚጠቀም በቀር በይዞታዉ ላይ የራሱን የመኖሪያ ቤት በመሥራትና ቋሚ አታክልትን በመትከል ይዞታዉን ቋሚ መኖሪያዉ ያደርጋል ተብሎ አይታሰብም፡፡ በአንጻሩ የአመልካች የመከላከያ ምስክሮች ይዞታዉ ለአመልካች ተሰጥቷቸዉ ለ30 ዓመታት የመኖሪያ ቤት ሠርተዉና ጫት ተክለዉ ሲጠቀሙ መቆየታቸዉን በመግለጽ ከተጠሪዎች ምስክሮች በተሻለ ሁኔታ አስረድተዋል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ አመልካች የክርክሩን ይዞታ የያዙት በተጠሪዎች አባት ፈቃድም ይሁን ያለ ፈቃዳቸዉ ይሁን ከ1983 ዓ/ም ጀምሮ በይዞታዉ ላይ ኑሮአቸዉን መሥርተዉና ከ1988 ዓ/ም ጀምሮ በስማቸዉ ግብር ከፍለዉ እንዲሁም የባለይዞታነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በስማቸዉ አዉጥተዉ የያዙት መሆኑ ክርክሩ በሥር ፍ/ቤቶች ሲደረግ በነበረበት ወቅት በየደረጃዉ ባሉ ፍ/ቤቶች በተሰበሰቡ የሰዉና የሰነድ ማስረጃዎች የተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች ይዞታዉን የያዙት ያለ ተጠሪዎች አባት ፈቃድ ቢሆን ኖሮ እንኳ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 36638፣ 105125 እና በሌሎችም መዝገቦች ከሰጣቸዉ አስገዳጅ ዉሳኔዎች አኳያ የይዞታዉ ባለመብት የሚሆኑ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ ምክንያቱም በአሁኑ ጊዜ በሥራ ላይ ካለዉ የመሬት ሥሪት አኳያ ማናቸዉም ሰዉ በአንድ ይዞታ ላይ ያለዉ መብት የባለይዞታነት መብት ብቻ እንጂ የባለርስትነት መብት ባለመሆኑ አመልካች የክርክሩን ይዞታ ለ30 ዓመታት ይዘዉ በይዞታዉ ላይ እንደ ጫትና ባሕር ዛፍ ያሉ ቋሚ አታክልትን ሲተክሉና ሰባት ክፍል የመኖሪያ ቤትን ሲሠሩ ያልተቃወሙት ተጠሪዎች ከ30 ዓመታት በኋላ ይዞታዉ እንዲለቀቅላቸዉ ሊጠይቁ የሚችሉበት የህግ አግባብ አይኖርምና ነዉ፡፡

ስለሆነም የምስራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ዉሳኔም ሆነ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባን ሰሚ ችሎትና ሰበር ሰሚ ችሎት ይህንን ዉሳኔ በማጽናት የሰጡት ትዕዛዝ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አስገዳጅ የሰበር ዉሳኔዎችን ጭምር የሚቃረን መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ስለተገኘ ስህተቱን በማረም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ዉሳኔ

1. የምስራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 104148 በ14/06/2015 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ምስራቅ ኦሮሚያ ቋሚ ምድብ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 417271 በ20/07/2015 ዓ/ም እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 422813 በ03/09/2015 ዓ/ም በዋሉ ችሎቶች በትዕዛዝ ያጸኑት ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በፍ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 348(1) መሠረት በሙሉ ድምጽ ተሽሯል፡፡

2. የሀረማያ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 87078 በ19/03/2015 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ ጸንቷል፡፡

3. አመልካች ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉን ይዞታ ለተጠሪዎች ሊለቁ አይገባም ተብሎ ተወስኗል፡፡

4. የዚህን ሰበር ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ በዉሳኔ ስለተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት እንዲመለስ ታዟል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ዉሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

የሰበር መ/ቁ/250546

ጥር 27 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች፡ ብርሃኑ አመነው

በእውቀቱ በላይ

መላኩ ካሳዬ

ማርታ ተካ

አየለ ማሞ

አመልካች፡- አቶ ኩማ መልኩ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ሰለሞን ዘለቀ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

መዝገቡ ለሰበር ችሎት የቀረበዉ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ የህግ ስህተት የለዉም በማለት በመ/ቁ/ 423754 ላይ በቀን 11/09/2015ዓ.ም የሰጠዉ ትእዛዝ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል በዚህ ሰበር ችሎት እንዲታረም በማለት አመልካች ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ሲታይ በስር ፍርድ ቤት አመልካቹ ከሳሽ ሲሆን ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን የተከራከሩ ሲሆን ጉዳዩ እርሻ መሬት ይዞታ የሚመለከት ነዉ፡፡አመልካች ሃምሌ 12 ቀን 2014ዓ.ም በዲጋሉና ጢጆ ወረዳ ፍርድ ቤት ባቀረበው አቤቱታ በዲጋሉ አራቢ ቀበሌ ውስጥ የሚገኘውን አዋሳኞቹ በክሱ የተጠቀሰ መሬት ከአያቴ ከበደ ዋቅጅራ እና ሴት አያቴ ወ/ሮ የሺ ተ/ማሪያም በመ/ቁ/43575 በሆነው በዉርስ ተወስኖልኝ በመ/ቁ 43575 ተፈጽሞልኝ እያለ ተጠሪ ምንም መብት ሳይኖረዉ ስለያዘብኝ እንዲለቅልኝ ሲል የጠየቀ ሲሆን ተጠሪ ጥቅምት 2 ቀን 2015 ዓ.ም ባቀረበው መልስ ይዞታው የአመልካች አያቶች ሳይሆን በቅይይር ከአቶ ታደሰ ከበደ ያገኘሁት የግል ይዞታዬ ነው፤የተቀያየርነውን ይዞታ ሰዎች ተቀብለው የመኖሪያ ቤት የሰሩበት ሲሆን እኔም ይዞታውን እየተጠቀምኩበት ስለሆነ ክሱ ተቀባይነት የለዉም በማለት ተከራክሯል፡፡

የወረዳ ፍርድ ቤትም ይዞታውን አመልካች በውርስ ያገኘው ነው ወይስ ተጠሪ በቅያሪ ያገኘው ነዉ? ይዞታው ከመሰረቱ የማን ነው? ስልጣን ያለው አካልስ ለማን ነው የሰጠው? የአቶ ታደሰ ከበደ ከሆነ በምን ሁኔታ እጁ ገባ? የሚሉ ጭብጦችን በመያዝ የግራቀኙን ምስክር ከሰማ በኃላ ተጠሪ ይዞታውን ስልጣን ባለው አካል አግኝቶ በቀን 14/10/2009ዓ.ም በተፃፈ ስምምነት በቅያሪ ያገኘ ስለመሆኑ ተገንዝበናል፤ስምምነቱ በአግባቡ የተደረገ ሲሆን ይዞታው በአቶ ታደሰ ከበደ እጅ መግባቱን ተረድተናል፤በመሆኑም አመልካች በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ/33(2)(3) መሰረት መብት የለውም ሲል ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡

አመልካች በውሳኔው ላይ ይግባኝ ለአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ይዞታው ከወረዳ እና ቀበሌ በመጡት ኮሚቴ የውርስ ንብረቱ ሲጣራ ተጠሪ እያየ እንደነበር እየገለፀ በሌላ በኩል ሲካሄድ በነበረው ክርክር ውስጥ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/41 ወይም ከውሳኔ በኃላ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/358 መሰረት ጣልቃ በመግባት መብቱን ማስከበር እየቻለ አመልካች አርሶና ዘርቶ ያዘጋጀውን መሬት በጉልበት በመያዝ በቅያሪ ነው ያገኘሁት በሚል ያነሳው ክርክር ተቀባይነት የለውም ሲል የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በመሻር ይዞታውን ለአመልካች እንዲለቅ ወስኗል፡፡ተጠሪም ውሳኔውን ተቃውሞ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ መሬቱን አቶ ታደሰ ከበደ ከአያቶቹ ላይ የመዉረስ መብት አለዉ፤መብት ካለዉ ሰዉ ላይ በቅያሪ ያገኘዉን መሬት ሊለቅ አይገባም በሚል ምክንያት የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ሽሮ የወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ ያፀና ሲሆን አመልካች አቤቱታ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ችሎቱ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት አልተፈፀመም ሲል መዝገቡን ዘግቷል፡፡ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ነዉ፡፡

አመልካች ሃምሌ 10 ቀን 2015 ዓ.ም ባቀረበው የሰበር አቤቱታ ይዞታውን በውርስ ያገኘሁት ስለመሆኑ በምስክር ተረጋግጦልኝ እያለ ክሱን ለማቅረብ መብት የለህም ተብዬ ክስ ውድቅ መደረጉ ስህተት ነው፤የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ካስፈፀመ በኃላ ተጠሪ በጉልበት የያዘውን መሬት በቅያሪ ነው ያገኘው በማለት ከቀድሞ ውሳኔና አፈፃፀም ተቃራኒ የሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት ነው፤የድጋሉ እና ጢጆ ወረዳ ፍርድ ቤት ፍርድ ሲሰጥ በድጋሉ እና ጢጆ ወረዳ መሬት አስተዳደር የተፀፈውን ደብዳቤ ሳይተነትን ነው፤የወረዳው ፍርድ ቤት አቶ ታደሰ እና ባለቤታቸው በመጥሪያ ጠርቶ አለመቅረባቸውን በውሳኔ ውስጥ ባልጠቀሰበት ሁኔታ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጠርተው ቀርተዋል በማለት በውሳኔ ላይ መጥቀሱ እንዲሁም ውሉ በወረዳው መሬትና አከባቢ ጥበቃ ቀርቦ ባልፀደቀበት ሁኔታ መወሰናቸው ስህተት ነው፤ በመሆኑም የወረዳው ፍርድ ቤት በመ/ቁ42544 በሆነው ወስኖልኝ በመ/ቁ/43575 ላይ ያስፈፀመውን የራሱን ውሳኔ መሻሩ ስህተት ሲሆን የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንዲሁም ሰበር ሰሚ ችሎቱ ውሳኔውን ማፅናታቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ውሳኔው ተሽሮ በአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ እንዲፀናልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

የሰበር ችሎቱ አቤቱታውን ከመረመረ በኃላ አመልካች ይዞታውን በተመለከተ በስር ፍርድ ቤቶች በመ/ቁ/42544 አስወስኖ በመ/ቁ/43575 በአፈፃፀም የተረከበው መሬት መሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች ከመረጋገጡ አንፃር አንዱን ስንጋ(ወሎ) መሬት ተጠሪው ለአመልካች ሊለቅ አይገባም ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለማጣራት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ በጥቅምት 27 ቀን 2017ዓ.ም ያዘዘ ሲሆን ተጠሪ በታህሳስ 1 ቀን 2017ዓ.ም ባቀረበው መልስ የእርሻ መሬቱ የአቶ ታደሰ ከበደ የውርስ ድርሻ ሲሆን ይህም በህግ አግባብ ግንቦት14 ቀን 2009ዓ.ም በተደረገ የለውጥ ውል ወደ ተጠሪ የተዛወረ ነው፤አመልካች በውርስ ያገኘው 2 ጥማድ መሬት ሳይሆን 1 ጥማድ ነው ይህም በእጁ መኖሩ የተረጋገጠ ስለሆነ የስር ፍርድ ቤት አቤቱታውን ውድቅ ያደረገበት መንገድ ፍትሀዊ ነው፤የገጠር መሬት ላይ ፍርዱ ተፈፀመ የሚባለው ለመሬቱ ህጋዊ ባለቤትነት ማስረጃ ሲሰጠው እንደሆነ በሰ/መ/ቁ/101079 አስገዳጅ ውሳኔ የተሰጠ ሲሆን አመልካች ባልተፈፀመና መብት በሌለው መሬት ላይ ክስ መስርቶ ውድቅ መደረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ በዲጋሉ ጢጆ ወረዳ ፍርድ ቤት፤በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንዲሁም በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ እንዲፀና በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች የመልስ መልሱን ታህሳስ 15 ቀን 2016 ዓ.ም አቅርቧል ፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ያስቀርባል ሲባል የተያዘውን ጭብጥ ከግራቀኙ ክርክር፤በስር ፍርድ ቤት በማስረጃ ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር እና ከተገቢው የህግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡አቤቱታ ለሰበር የቀረበዉ አመልካች ይዞታውን በተመለከተ በስር ፍርድ ቤቶች በመ/ቁ/42544 አስወስኖ በመ/ቁ/43575 በአፈፃፀም የተረከበው መሬት መሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች ከመረጋገጡ አንፃር አንዱን ስንጋ(ወሎ) መሬት ተጠሪው ለአመልካች ሊለቅ አይገባም ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለማጣራት ነዉ፡፡መዝገቡን መርመረን እንደተገነዘብነዉ አመልካቹ ዳኝነት የጠየቀዉ አዋሳኙ በክሱ ዝርዝር የተገለጸዉን መሬት ከአያቱ አቶ ከበደ ዋቅጅራ እና ሴት አያቱ ወ/ሮ የሺ ተ/ማርያም በዉርስ አግኝቶ በመ/ቁ42544 ተወስኖ በመ/ቁ 43575 ላይ የተፈጸመለት መሆኑን እና ተጠሪ መብት ሳይኖረዉ ይዟል የሚል ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ መሬቱ የአመልካቹ ሳይሆን የአቶ ታደሰ ከበደ እና ወ/ሮ ከበቡ ብሪ ስለመሆኑ እና በቀን 14/10/2009ዓ.ም በተደረገ ስምምነት በቅያሪ ያገኝ ስለመሆኑ ገልጾ መከራከሩን መዝገቡ ያሣያል፡፡ይሁንና የወረዳ ፍርድ ቤት ለክርክር ምክንያት የሆነዉ መሬት ተጠሪ በለዉጥ ያገኘዉ ነዉ በማለት አመልካች በዚህ ላይ ክስ የማቅረብ መብት የለዉም የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡የበላይ ፍርድ ቤቶች በበኩላቸዉ በፍሬነገር ረገድ ማስረጃ መርምረዉ የተለያየ አቋም ላይ መድረሳቸዉን ከላይ ባጭሩ ተመልክተናል፡፡

ስለሆነም በቀዳሚነት መነሳት የሚገባዉ መሰረታዊ ጉዳይ የስር ፍርድ ቤቶች ክርክሩን የመሩበት አግባብ ስነስርዓቱን የተከተለ ነዉ ወይ የሚለዉ ነዉ፡፡በህግ በሌላ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር የፍትሃብሔር ክርክር የሚመራዉ በፍትሃብሔር ስነስርዓት ህግ በተደነገገዉ ስርዓት መሰረት ነዉ፡፡የፍትሐብሔር ስነስርዓት ህግ የተዘረጋበት ዋነኛ ዓላማ ክርክሮች በስርዓት እንዲመሩ ማድረግ አንጻራዊ እዉነትን ማፈላግ እና በአነስተኛ ወጪ፤ ጊዜ፤እና ሀብት ለክርክሩ ዉጤታማ እልባት መስጠት ነዉ፡፡ለዚህም ከሳሽ ወገን የሚጠይቀዉን ዳኝነት ወይም መፍትሔ (relief) በግልጽ እና በዝርዝር በአቤቱታዉ እንዲገለጽ የሚያስገድድ ድንጋጌ ተካቶ እናገኛለን፡፡ይህ ስርዓት ዳኝነት ሰጪ አካልም ክርክሩን በአግባቡ በመምራት አከራካሪዉን ፍሬነገር ለይቶ እና በማስረጃ አጣርቶ እንዲሁም ህጉን አገናዝቦ ተገቢዉን መፍትሄ መስጠት ያስችለዋል ተብሎ ይታሰባል፡፡ይህንን ከማረጋገጥ አንጻር በህጉ ከተዘረጋዉ ስርዓት አንዱ ከሳሽን እና ተከሳሽ ያከራከረዉ የፍሬነገር ወይም የህግ ጉዳይ በመለየት ተገቢዉን ጭብጥ በመያዝ በማስረጃ አጣርቶ ዉሳኔ ላይ መድረስ ያስችላል፡፡ስለጭብጥ አመሰራረት

በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 246 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች የተዘረዘረዉ በመመርመር ይህንኑ ያስገነዝባል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ከክርክሩ መገንዘብ እንደቻልነዉ ለክርክር ምክንያት የሆነዉን መሬት ተጠሪ መያዙ አልተካደም ብቻ ሳይሆን በማስረጃም የተረጋገጠ ነዉ፡፡ነገር ግን ተጠሪ መሬቱን የያዘዉ በለዉጥ ነዉ የሚል ሲሆን በሌላ በኩል በለዉጥ ሰጠ የተባለዉ ሰዉ ላይ አመልካች ክስ አቅርቦ በመ/ቁ 42544 ማስወሰኑን እና በመ/ቁ/ 43575 ማስፈጸሙን ገልጾ ተከራክሯል፡፡ይህ ከሆነ ደግሞ በለዉጥ የተያዘዉ መሬት እና አመልካቹ በፍርድ አገኘሁ የሚለዉ መሬት አንድ ነዉ ወይስ አይደለም የሚለዉ እንዲሁም በለዉጥ ሰጠ የተባለዉ ሰዉ መብት አለዉ ወይስ የለዉም የሚለዉ ነጥብ በጭብጥነት ተይዞ መጣራት ያለበት ጉዳይ ነዉ፡፡ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለተጠሪ መሬት በለዉጥ ሰጥቷል የተባለዉ አቶ ታደሰ ከበደ የአያቶቹን መሬት የመዉረስ መብት አለዉ በሚል ምክንያት የወረዳ ፍርድ ቤት ዉሳኔ ማጽናቱን ዉሳኔዉ ያሣያል፡፡ይሁንና አቶ ታደሰ ከበደ የክርክሩ ተካፋይ ባልሆነበት እና የዉራሽነት መብት ያለዉ ስለመሆኑ ክርክርም ሆነ ማስረጃ ባልቀረበበት ሁኔታ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከዚህ ድምዳሜ የደረሰበት ሁኔታ ግልጽ አይደለም፡፡በሌላ በኩል አመልካቹ አቶ ታደሰ ከበደ ላይ ክስ አቅርቦ ያስወሰነ ስለመሆኑ መ/ቁ42544 ጠቅሶ ተከራክሯል፡፡በዚህ አግባብ አልተወሰነም ተብሎ የቀረበ ማስተባበያ መኖሩ አልተረጋገጠም፡፡በሌላ አገላለጽ አመልካቹ በፍርድ አገኘዉ የሚለዉ መብት ስርዓት ጠብቆ የተሻረ ስለመሆኑ ክርክር አልቀረበም፡፡ስለሆነም አሁን ክርክር የተነሳበት መሬት አመልካቹ በፍርድ ያገኘዉ መሆን አለመሆኑ እና የተሻለ መብት ያለዉ ማነዉ የሚለዉን ለመለየት መጣራት የሚገባ ነጥብ መኖሩን ያሣያል፡፡ከዚህ አኳያ በጭብጥነት ተይዞ መጣራት ያለበት ነጥብ አመልካቹ ከአቶ ታደሰ ከበደ ጋር የተከራክሮ በፍርድ መብት ያገኘበት መሬት እና ተጠሪ በለዉጥ ከአቶ ታደሰ ከበደ አገኘሁ የሚለዉ መሬት አንድ ነዉ ወይስ አይደለም፤አንድ ነዉ ከተባለ ለተጠሪ በለዉጥ የሰጠዉ አቶ ተደሰ ከበደ ህጋዊ መብት አለዉ ወይ? የሚለዉን እና በአከራካሪዉ መሬት ላይ በፍርድ አገኘዉ ከሚለዉ አመልካች እና በለዉጥ ያዝኩት ከሚለዉ ተጠሪ ማን የተሻለ መብት አለዉ? የሚለዉን በማጣራት እንዲሁም አንጻራዊ እዉነትን ከመዉጣት አኳያ አቶ ታደሰ ከበደ የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆን በማድረግ ጉዳዩን በአግባቡ አጣርቶ መወሰን አስፈላጊ ነዉ፡፡ከዚህ አንጻር አቶ ከበደ ታደሰ የክርክሩ ተካፋይ ባልሆነበት እና መብቱን ባላስረዳበት ሁኔታ ወራሽነት መብት አለዉ ተብሎ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የደረሰበት ድምዳሜ ሲታይ ክርክሩ የተመራበት አግባብ የክርክር አመራር ስርዓት ጉድለት ያለበት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ከዚህ ጋር በተያያዘ ሰበር ችሎቱ በተለያዩ

መዝገቦች ላይ በሰጠዉ ገዥ ዉሳኔ እንዳመላከተዉ በተከራካሪ ወገን የቀረበ ክርክር አግባብነት ያለዉ ጭብጥ ሳይያዝ እና አግባብነት ባለዉ ማስረጃ በተሟላ ሁኔታ ሳይጣራ የሚሰጥ ዉሳኔ መሰረታዊ ክርክር አመራር ጉድለት ስለመሆኑ እና በሰበር ችሎቱ ሊታረም የሚገባ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ሰበር መ/ቁ/43845፤37105 እና ሌሎች መዝገቦችን ይመለከቷል፡፡

ሲጠቃለል ግራቀችን እያከራከረ ያለዉ መሬት ተጠሪ ለአመልካቹ ሊለቅ ይገባል ወይስ አይገባም የሚለዉን ለመወሰን ይቻል ዘንድ ተገቢዉ ጭብጥ በመያዝ እና መሬቱን በለዉጥ ለተጠሪ ሰጥቷል የተባለዉ ሰዉ ወደ ክርክሩ እንዲገባ ሳይደረግ እና አመልካቹ በፍርድ ያገኘዉ መብት በሌላ ህጋዊ ምክንያት መሻሩ ሳይረጋገጥ ዉጤት የሚያጣበት ሁኔታ በመፍጠሩ ፍርድ ቤቶቹ የደረሱበት ድምዳሜ በክርክር አመራር ረገድ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ስለሆነም አከራከሪዉ መሬት ላይ የተሻለ መብት የተፈጠረለት ማነዉ የሚለዉ ሳይጣራ ለክርክር ምክንያት የሆነዉን መሬት የወራሽነት መብት ካለዉ ሰዉ ላይ ተጠሪ በለዉጥ ያገኘዉ ነዉ በሚል ምክንያት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ፍርድ እና ይህንኑ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ትእዛዝ ተገቢ ጭብጥ ተይዞ ሳይጣራ ከድምዳሜ የደረሰ በመሆኑ የክርክር አመራር ስርዓት ጉድለት ያለበትና ሰበር ችሎቱ የሰጠዉን ገዥ ዉሳኔ የሚቃረን በመሆኑ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4ሐ እና ሸ) እና 10(1/ሐ) መሰረት መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ብለናል፡፡ በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ዉሳኔ

1. በዚህ ጉዳይ የዲጋሉና ጢጆ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/44803 ላይ በቀን 15/03/2015ዓ.ም የሰጠዉ ፍርድ፣የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/106607 ላይ በቀን 13/04/2015ዓ.ም የሰጠዉ ፍርድ፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና ሰበር ሰሚ ችሎት በቅደም ተከተል በመ/ቁ 415878 እና 423754 ላይ የሰጡት ዉሳኔ በሰበር ስነስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የዲጋሉና ጢጆ ወረዳ ፍርድ ቤት መዝገቡን በማንቀሳቀስ ከላይ በፍርድ ሀተታ ላይ በተገለጸዉ እና ተያያዥ ጭብጥ ላይ ግራቀኝ በማከራከር እና አግባብነት ባለዉ ማስረጃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

በማጣራት ተገቢዉን እንዲወስን በማለት መዝገቡን በሰበር ስነስርዓት መመሪያ አንቀጽ 9(2) መሰረት መልሰንለታል፡፡ይጻፍ

3. ሰበር ችሎቱ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

መ/ዐ                                        የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 250597

ጥር 26 ቀን 2017ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ሽመክት አሰፋ

በዕውቀት በላይ

መላኩ ካሳዬ

ማርታ ተካ

አመልካቾች፡- 1. ወ/ሮ ዘውዲቱ ድንቁ

2. አቶ ዳዊት ድንቁ

ተጠሪ፡- የቀድሞ አርጋፋ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት (በአሁን አርጋፋ ማዘጋጃ ቤት)

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሐምሌ 03 ቀን 2015ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 26960፤ ጥቅምት 28 ቀን 2015 የሰጠው ውሳኔ እና ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 42102፤ ሚያዝያ 03 ቀን 2015ዓ.ም መወሰኑ የመሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 6 መሠረት የቀረበን የዳግም ዳኝነት ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ከመነሻው በዋናው ጉዳይ ክርክር የተጀመረው በኦሮሚያ ክልል አጋርፋ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካች ከሳሽ፤ የአሁን ተጠሪ ተከሳሽ ነበሩ፡፡

የአሁን አመልካች በአሁን ተጠሪ ላይ ያቀረቡትን ክስ የአሁኑ ተጠሪ ያረጁ የቀበሌ ቤቶችን ምትክ ቤት በመስራት የቀበሌው ቤት የነበረበትን ቦታ ተረክቦ ለማልማት ለሚችል ወገን ባወጣው ጨረታ ላይ አመልካቾች ተወዳድረን 1ኛ አመልካች የቤት ቁጥር 0034 በማሸነፍ ተጠሪ በቀበሌ ቤት ምትክ የሚሰራበትን ቦታ አዘጋጅቶ እስኪሰጠኝ ድረስ የቤት መስሪያ ፈቃድ ተሰጥቶኝ አንድ ትልቅ ቤትና ትንንሽ ሰርቪስ ቤቶች በጥቅሉ 100 ቆርቆሮ ቤቶች በጨረታ ባሸነፍኩበት ቦታ ላይ ሰርቼ ከዘጠኝ አመት በላይ በእጄ ቆይቷል በመሆኑም ተጠሪ በገባው ውል ስምምነት መሰረት እንዲፈጽምና ለቀበሌ ቤት ምትክ የምሰራበትን ቦታ እንዲሰጠኝ፤ 2ኛ አመልካችም ደግሞ በአጋርፋ ከተማ አስተዳደር 01 ቀበሌ ውስጥ የሚገኝ ጨረታ ያሸነፍኩበትን ውል እንዲፈጽምልኝ በሚል ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ በሰጠው መልስ አመልካቾች በ2000ዓ.ም ውስጥ በጨረታ አሸንፈናል ቢሉም ውል ስለመኖሩ በማስረጃነት አላቀረቡም፤ ጨረታ አሸነፍን በሚሉበት ጊዜ እንደ ሌሎች ሰዎች ግንባታውን ቢፈጽሙ ኖሮ ተቃውሞ አይኖረንም ነበር ሆኖም ከዘጠኝ አመታት በኃላ በሰሩት ቤት ምትክ ቦታ ለመውሰድ የሊዝ አዋጁም ሆነ ደንብ ቁጥር 155/2005 እና በመመሪያ ቁጥር 10/2006 መሰረት ህጉ የማይፈቅድ በመሆኑ ክሱ ተገቢነት የለውም በሚል ተከራክረዋል፡፡

በወረዳው ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ግራቀኙን አከራክሮና ከሚመለከተው አካል ማጣራት ካደረገ በኃላ የአሁኑ አመልካቾች ተጠሪ ባወጣው ጨረታ ማሸነፋቸውና ውል ያለ ስለመሆኑ በሰው ምስክር እና በተደረገው ማጣራት ከቀረበው የጽሁፍ ማስረጃ ተረጋግጧል በማለት የአሁኑ ተጠሪ በውሉ መሰረት ሊፈጽም ይገባል በማለት በመ/ቁ 17483፤ በቀን 26/10/2010ዓ.ም ወስኗል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ ይህንኑ የወረዳው ፍ/ቤት ውሳኔ በመቃወም ይግባኙ ለባሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱም የአሁኑ አመልካቾች ከተጠሪ ጋር የውል ስምምነት አድርገናል ቢሉም ከመንግስት አስተዳደር አካል ጋር የሚደረግ ማንኛውም ውል በጽሁፍ ሊሆን እንደሚገባ ህጉ የሚደነግግ ሆኖ እያለ፤ በአሁኑ አመልካቾች በኩል ውል ባልቀረበበት ሁኔታ ተጠሪ ውሉን ይፈጽም ተብሎ መወሰኑ ተገቢ አደለም በሚል የወረዳው ፍ/ቤት ውሳኔ በመሻር የአሁኑ አመልካቾ ክስ ውድቅ በማድረግ በመ/ቁ 26960፤ በቀን 03/04/2011ዓ.ም ወስኗል፡፡

የአሁኑ አመልካቾች ይህንኑ የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፍርድ በመቃወም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 6 መሠረት የዳግም ዳኝነት ጥያቄ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፡- ተጠሪ ውሉን በመደበቅ ውል ሳይኖር ውል

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

ለመፈፀም አንገደድም በሚል ሲከራከርና ለፍ/ቤት ምላሽ በመስጠቱ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት አመልካቾች ውሉን አላቀረቡም በሚል ክሳችን ውድቅ ያደረገ ቢሆንም የአርጋፋ ወረዳ ፖሊስ ጽ/ቤት በ25/9/2014ዓ.ም በጻፈው ደብዳቤ የአሁኑ አመልካቾች ከተጠሪ ጋር በጽሁፍ ያደረጉት ውል የድምጻዊ ሐጫሉ ሁንዴሳ ሞት በተሰማበት ወቅት በወረዳው ሁከት ተነስቶ በተነሳው ቃጠሎ በተጠሪ ተቋም የነበሩት ሰነዶች ሲቃጠሉ ይህ የውል ሰነድ ግን ከቃጠሎው ከተረፉት የተጠሪ መ/ቤት ቀሪ ሰነዶች ጋር ተያይዞ የተገኘ መሆኑን የገለፀላቸው መሆኑን በማረጋገጥ በተጠሪ መ/ቤት ውስጥ የውል ሰነድ እያለ የለም በሚል ሀሰተኛ መረጃ መስጠቱ ወንጀል ጠቀስ ተግባር መሆኑን ጠቅሶ የውል ሰነድ በተጠሪ ተቋም ውስጥ ስለተገኘ በዳግም ዳኝነት ታይቶ የስር ወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲፀናልን የሚል ነው፡፡

የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካቾች ባቀረቡት የዳግም ዳኝነት ጥያቄ ላይ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዞ ተጠርቶ ባለመቅረቡ መልስ የመስጠት መብቱ በማለፍ የአመልካቾች የዳግም ዳኝነት ይታይልን ጥያቄ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 6 ድንጋጌ መስፈርቶች አያሟላም በሚል አቤቱታቸውን ውድቅ በማድረግ በመ/ቁ 26960፤ በቀን 28/2/2015ዓ.ም ወስኗል፡፡

በመቀጠል አመልካቾች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ በማጽናት በመ/ቁ 42102፤ በቀን 03/8/2015ዓ.ም ወስኗል፡፡

የአሁኑ አመልካቾች ሐምሌ 03 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይዘቱ ሲታይ፡- አመልካቾች ጥቅምት 15 ቀን 2000ዓ.ም ከተጠሪ ጋር ያደረግነው የውል ሰነድ ከተጠሪ መ/ቤት ጋር የሚገኝ መሆኑን ገልጸን ስንከራከር የወረዳው ፍ/ቤት የውል ሰነዱ እንዲቀርብ ለተጠሪ ትእዛዝ ሲሰጥ ተጠሪ ተቋም ውሉን በመደበቅ የውል ሰነድ የለም በሚል ምላሽ መስጠቱ ሀሰተኛ መረጃ ለፍ/ቤት መስጠቱን የሚያሳይ በሆነበት፤ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የውል ሰነድ አልቀረበም በሚል ከወሰነ በኃላ የፖሊስ ጽ/ቤቱ በ15/2/2015ዓ.ም በጻፈው ደብዳቤ በአጋርፋ ከተማ ከአርቲስት ሀጫሉ ሁንዴሳ ሞት በኃላ በተነሳ ሁከት በከተማው የሚገኙ የመንግስት መ/ቤቶች በመቃጠላቸው ምክንያት ተጠሪ መ/ቤትም የዚህ ቃጠሎ ተጠቂ የነበረ ቢሆንም በወረዳው ፖሊስ ጽ/ቤት በኩል ከቃጠሎ የተረፉ የተጠሪ መ/ቤት መዛግብት ሲሰበሰብ ጥቅምት 15 ቀን 200ዓ.ም የተረገው ውል እና ምትክ ቦታ እንዲሰጣቸው አመልካቾች የጠየቁበት ሰነድ ጭምር በተጠሪ መ/ቤት መዛግብት ውስጥ ተያይዞ የተገኘ መሆኑ አረጋግጦ እያለ፤ ተጠሪ የውል ሰነዱ እያለ በተቋሙ ውስጥ የለም በሚል መረጃ ለፍ/ቤት በመስጠቱ፤ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 380 እና 381 የሰነድ ማስረጃው ተደብቆ የተገኘ መረጃ መሆኑ

ወንጀል ጠቀስ ድርጊት ሆኖ እያለና ከዚህ ጋር በተያያዘ በሰ/መ/ቁ 91968(ቅጽ 15 የታተመ) ላይ ገዢ የህግ ትርጉም በሰጠበት ሁኔታ የሰበር ውሳኔው በሚቃረን ሁኔታ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቤቱታችን የህጉን መስፈርት አያሟላም በሚል መወሰኑም ሆነ ተጠሪ ውሉ ደብቆት መቆየቱ ወንጀል ጠቀስ ተግባር መሆኑን ጠቅሰን በስር ፍ/ቤት ተከራክረን እያለ በክልሉ ሰበር ሰሚ ፍ/ቤት በስር ያልተነሳ አዲስ መከራከርያ ነው ተብሎ የስር ውሳኔ በማጽናት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ አመልካቾች በግራቀኙ መሀከል ጥቅምት 15 ቀን 2000ዓ.ም የተደረገው የውል ሰነድ ማቅረብ አልቻሉም በሚል የዳኝነት ጥያቄያቸው ውድቅ የተደረገ ቢሆንም የአጋርፋ ወረዳ ፖሊስ ጽ/ቤት በቁጥር 354/07/2014፤ ሰኔ 03 ቀን 2014ዓ.ም በጻፈው ደብዳቤ በተጠሪ ተቋም ውስጥ ካልተቃጠሉ መዝገቦች ውስጥ የውል ሰነዱ ተያይዞ የተገኘ መሆኑን የገለጸላቸው መሆኑን በማረጋገጥ ያቀረቡት የድጋሚ ዳኝነት ይታይልኝ አቤቱታቸው ስር ውድቅ የመደረጉን ተገቢነት ተጠሪ አስተዳደር አካል ጭምር ሆኖ ውሉ አልተደረገም በሚል ከማረጋገጡ፣ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ.ቁ 6 ድንጋጌ እና ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 91968 ከሰጠው ትርጉም አንጻር ለማጣራት ሲባል ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ታዞ ተጠሪ መጥሪያ ደርሶት ባለመቅረቡ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተመለከተዉን የሚመስል ሲሆን ከስር ፍ/ቤት ዉሳኔ እና ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ተብሎ ከተያዘዉ ጭብጥ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡
በመሠረቱ ማንኛውም ሰው ፍርድ ቢሰጥበት በሕጉ በተመለከቱት ምክንያቶች ብቻ ፍርዱን ለፈረደው ፍ/ቤት የተወሰነውን ዳኝነት በመክፈል ድጋሚ ዳኝነት እንዲታይለት መጠየቅ እንደሚችል፤እነኚህም ምክንያቶች የመጨረሻው ፍርድ የተሠጠው በሐሰት ተዘጋጅቶ የቀረበውን ሠነድ ወይም ሐሰተኛ የምስክርነት ቃልን ወይም መደለያን ወይም ወንጀል ጠቀስ የሆነ ተግባርን መሠረት በማድረግ ሲሆን እና አቤት ባዩም ፍርድ ከመሠጠቱ በፊት አስፈላጊውን ትጋት አድርጎ ለማወቅ ያለመቻሉን ለማስረዳት የቻለ እንደሆነ፤እነዚህ ተግባሮች መፈጸማቸው ቢገለጽ ኖሮ ፤ለፍርዱ መለወጥ ወይም መሻሻል ምክንያት ሊሆኑ ይችሉ እንደነበር ማስረዳት የተቻለ እንደሆነ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 6 ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 112258፤ 115377 እና በሌሎችም መዛግብት በሰጠው ውሳኔ የሚመለከተው የአስተዳደር አካል በሰጠው ምላሽ መነሻነት የተሰጠን ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 6 ላይ በተቀመጡት ሁኔታዎች ተገቢ

ያልሆነ ማስረጃ ቀርቦ የተሰጠ ውሳኔ መኖሩ ካልተረጋገጠ በቀር በዳግም ዳኝነት አስቀድሞ የተሰጠን ውሳኔ መሻር እንደማይቻል በመግለጽ አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም የሰጠ ሲሆን በሌላ በኩል አንድ የመንግስት አካል እውነተኛውን ሳያጣራ መስጠት የማይገባውን ሀሰተኛ ማስረጃ ለፍርድ ቤት በመስጠቱ ውሳኔ የተሰጠበት ወገን ማስረጃው ሀሰተኛ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ እስካቀረበ ድረስ የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 6/1/ መስፈርትን አያሟላም ሊባል እንደማይገባና አቤቱታ አቅራቢው ሀሰተኛ መረጃ የተሰጠው በመንግስት አካል መሆኑን ከማስረዳት አልፎ የመንግስት አካሉ ይህንን ህገወጥ ተግባር የፈፀመበትን ምክንያት ማስረዳት እንደማይጠበቅበት ጭምር በሰ/መ/ቁ 91968(ቅጽ 15 የታተመ) ላይ ገዢ የህግ ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ የወረዳው ፍርድ ቤት አመልካቾች ጨረታ በማሸነፍ ከተጠሪ ጋር ውል መግባታቸውን በምስክሮችና በተደረገ ማጣራት ተረጋግጧል በማለት ተጠሪ በገባው ውል መሰረት ሊፈጽም ይገባል በማለት የወሰነውን የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሻረበት ምክንያት ተጠሪ አስተዳደር አካል ከመሆኑ አኳያ በአመልካቾች የውል ሰነድ ባልቀረበበት ሁኔታ ተጠሪ በውሉ መሰረት እንዲፈጽም አይገደድም በሚል ነው፡፡ ተጠሪ መ/ቤት የአስተዳደር አካል ጭምር ከመሆኑ አኳያ በስር ፍርድ ቤቶች በነበረው ክርክር በግራቀኙ መሀከል ውል እንዳልተደረገ በማረጋገጥ ለፍ/ቤት ምላሽ ሲሰጥ መቆየቱና የወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለባሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲያቀርብም አመልካቾች ከተጠሪ መ/ቤት ጋር ያደረጉት ውል ስለመኖሩ ሳይረጋገጥ ውል እንድንፈጽም መወሰኑ ተገቢ አደለም በሚል መከራከሩን ያሳያል፡፡

አመልካቾች የዳግም ዳኝነት ይታይልን አቤቱታቸውን ለባሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲያቀርቡ ምክንያታቸው አመልካቾች ጥቅምት 15 ቀን 2000ዓ.ም የተደረገው የውል ሰነድ ማቅረብ አልቻሉም በሚል ክሳቸውን ውድቅ በማድረግ ውሳኔ ሊሰጥ የቻለው ተጠሪ የአስተዳደር አካል ጭምር ሆኖ ውሉ በተቋሙ ስር በሚገኙ መዛግብት ተያይዞ እያለ ውሉን በመደበቁና ውሉ አልተደረገም በሚል በማረጋገጥ ለፍ/ቤት ሀሰተኛ መረጃ በመስጠቱ መሆኑን፤ ይሁን እንጂ ከአመልካቾች ጋር የተደረገ ውል ሰነዱ በተጠሪ መ/ቤት ውስጥ ከሚገኙ ካልተቃጠሉ ቀሪ መዝገቦች ውስጥ ተያይዞ መገኘቱን የአጋርፋ ወረዳ ፖሊስ ጽ/ቤት በቁጥር 354/07/2014፤ሰኔ 03 ቀን 2014ዓ.ም በጻፈው ደብዳቤ መረጋገጡን፣ የውል ሰነዱ በተጠሪ ተቋም ስር ስለመኖሩ በወረዳው ፖሊስ ጽ/ቤት የተነገራቸውም በ3/10/2014ዓ.ም መሆኑን በመግለጽ ነው፡፡

በስር ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር ተጠሪ ስር ተከሳሽ በመሆን እና የአስተዳደር አካል ጭምር ሆኖ በአመልካቾች እና ተጠሪ መሀከል ጥቅምት 15 ቀን 2000ዓ.ም የተደረገ ውል ስምምነት እያለ በተጠሪ

ተቋም መዛግብት ውስጥ በግራቀኙ መሀከል የተደረገ የውል ሰነድ እንደሌለ በማረጋገጥ ለፍ/ቤት በዚህ አግባብ ሲከራከርና ምላሽ ሲሰጥ የቆየ ቢሆንም ቀድሞውንም ይህ የውል ሰነድ በተጠሪ ተቋም ውስጥ በሚገኙ መዛግብት ውስጥ ተያይዞ የነበረ ስለመሆኑ ከወረዳው ፖሊስ ጽ/ቤት በኩል ከተጻፈው ደብዳቤ የምንረዳው ነው፡፡ ተጠሪ መ/ቤት የውል ሰነዱ በአስተዳደር ተቋሙ ስለመኖሩ እያወቀ ከአመልካቾች ጋር የተደረገ ውል እንደሌለ በማረጋገጥ መረጃ ለፍ/ቤት መስጠቱና ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትም ጉዳዩን በይግባኝ አይቶ የአመልካቾች ክስ ውድቅ ያደረገው አመልካቾች የውል ሰነዱን ማቅረብ አልቻሉም በሚል ምክንያት መሆኑን በዚህ መልኩ አመልካቾች ማስረዳት እስከቻሉ ድረስ የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ፍርዱን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ.ቁ 6(1) መሰረት እንደገና ለማየት በቂና ህጋዊ ምክንያት እያለው አመልካቾች ያቀረቡት የዳግም ዳኝነት ይታይልኝ ጥያቄያቸውን የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 6/1/ ስር የተመለከቱት የህጉ መስፈርትን አያሟላም በሚል ውድቅ ማደረጉና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም ይህንኑ ማጽናቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 6 የተዘረጋዉ ሥነ ሥርዓት ለማሳካት የታለመዉ ዓላማ ከግብ እንዳይደርስ የሚያደርግና ከላይ የተጠቀሱት ሰበር ውሳኔዎች የሚቃረን በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበትና ሊታረም የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1. የኦሮሚያ ክልል የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአመልካቾች የዳግም ዳኝነት ይታይልን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ በመ.ቁ 26960፤ በቀን 28/02/2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ እንዲሁም ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 421012፤በቀን 03/08/2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገቡን በማንቀሳቀስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ.ቁ 6 መሰረት ጉዳዩን በድጋሚ በማየት ጥቅምት 15 ቀን 2000ዓ.ም ተደረገ የተባለው የውል ሰነድ ቀርቦ አስቀድሞ ግራቀኙን ካደረጉት ክርክር እና ማስረጃ ጋር በመመዘን እንዲሁም በጉዳዩ ላይ ማጣራት ካስፈለገም ተገቢውን ማጣራት በማድረግ መርምሮ ህግን መሰረት ያደረገ ውሳኔ እንዲሰጥበት በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/2/ መሰረት መልሰን ልከናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

**ማስታወሻ**፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

**የሰ/መ/ቁ** 251591

**ጥር 27 ቀን 2017ዓ/ም**

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ

ሸመክት አሰፋ

በዕዉቀት በላይ

መላኩ ካሳዬ

ማርታ ተካ

**አመልካች**፡- የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ የመሬት ልማት አስተዳደር ጽ/ቤት

**ተጠሪ**፡- የአቶ አበበ ተመስገን ወራሾች

1. አቶ ብርሃኑ አበበ
2. ወ/ሮ ሰላማዊት አበበ
3. አቶ ዳንኤል አበበ
4. ወ/ሮ መሠረት አበበ
5. ወ/ሮ እየሩሳሌም አበበ
6. አቶ ብሩክ አበበ
7. ወ/ሮ ሃና አበበ
8. ወ/ሮ ሮዛ አበበ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነዉ ካርታ ተለዉጦ እንዲሰጥ የቀረበ የዳኝነት ጥያቄ ሲሆን የተጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ከሳሽ ሲሆኑ የአሁን አመልካች ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ በአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 251591 ጥቅምት 26 ቀን 2017 ዓ.ም ተሰጥቶ በየደረጃዉ ባሉት የከተማዉ ይግባኝ ሰሚ

የፍ/ቤት እና ሰበር ሰሚ ችሎት የጸናዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በሚል ነዉ፡፡

ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት፡- በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ወረዳ 6 የቤት ቁጥር 1963 የቦታ ስፋቱ 455 ካ.ሜትር የሆነ ይዞታ በ1976 ዓ.ም ከመንግስት በምሪት አግኝተዉ የግንባታ ፍቃድ በማዉጣት ቤት ሰርተዉ የካርታ ቁጥር 22091 የሆነ ካርታ ሰኔ 29 ቀን 1976 ዓ.ም ተሰጥቷቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች የቀድሞ ካርታዉን በአዲስ ለዉጦ ወይም ቀይሮ እንዲሰጣቸዉ ቢጠይቁም በተጠሪ ይዞታ ዉስጥ በGIS እና CIS የመረጃ ቋት ላይ የሚታይ ንብረትነቱ የመንግስት የሆነ የቀበሌ ቤት የቤት ቁጥር 346 ያለ በመሆኑ ተጠሪ የቀድሞ ካርታ ተመላሽ በማድረግ በተነጻጻሪ እንደሚሠራላቸዉ ያሳወቃቸዉ ቢሆንም በይዞታቸዉ ዉስጥ ምንም ዓይነት የቀበሌ ቤት በሌለበት በንጽጽር ካርታ የሚሠራበት የሕግ አግባብ ባለመኖሩ አመልካች በሕግ ተገዶ የቀድመዉን ካርታ በአዲስ ለዉጦ እንዲሰጣቸዉ እንዲወሰን የሚጠይቅ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካችም ለቀረበበት ክስ በሰጠዉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ጉዳይ መልስ ተጠሪ በይዞታዬ ላይ አዲስ ካርታ ተሰርቶ ይሰጠኝ የሚለዉ የመፋለም ክስ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለዉም፡፡ ጉዳዩ በአስተዳደር አካል ታይቶ መፍትሄ ማግኘት ያለበት እንጂ በመደበኛ ፍ/ቤት ታይቶ እልባት የሚሰጥበት ባለመሆኑ ክሱ ዉድቅ ሊደረግ ይገባል፡፡ ተጠሪ በጠየቁት መሠረት አዲስ ካርታ ሊሰጣቸዉ አይገባም፡፡ አስቀድሞ የተሰጣቸዉ ካርታ የተጠሪ የግል ይዞታና የቀበሌ ቤት ሳይለይ በደፈናዉ የተሰጠዉ ነዉ፡፡ በይዞታዉ ዉስጥ የቀበሌ ቤት የሆነዉን የቤት ቁጥር 346 ወ/ሮ ሊኬ ዳመሳ የሚባሉ ግለሰብ ከመንግስት ተከራይተዉ ሲጠቀሙበት እንደነበረ በወረዳዉ ወሳኝ ኩነቶች ተመዝግቦ የሚገኝ ከመሆኑም በላይ በGIS እና CIS የመረጃ ቋት የሚታይ በመሆኑ ነዉ፡፡ አመልካች አዲስ ካርታ ሰርቶ ለመስጠት ፍቃደኛ ሳይሆን ቀርቶ ሳይሆን ተጠሪ 455 ካ.ሜ ይዞታቸዉ ዉጪ የመንግስት ቤትና ይዞታ አስፋፍተዉ በመያዝ 845 ካ.ሜ ላይ ካርታ እንዲሠራላቸዉ በመጠየቃቸዉ ነዉ፡፡ ስለሆነም ተጠሪ የበፊቱን ካርታ ሳይመልሱ እና ከይዞታቸዉ ዉጪ ያለዉን የመንግስት ቤትና ቦታ ሳይለይ አዲስ ካርታ ሊሰጣቸዉ ስለማይችል የመንግስት ይዞታ በልኬት ተለይቶ እንዲወሰን በመጠየቅ ተከራክሯል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካችን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን ዉድቅ በማድረግ ግራ ቀኙን አከራክሮና የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቤቶች ልማት አስተዳደር ጽ/ቤት፤ የወረዳ 6 ቤቶች ልማት ጽ/ቤት እና የክ/ከተማዉ መሬት ልማት ጽ/ቤት በጋራ በመሆን ለክርክር መነሻ በሆነዉ ቦታ ባለሙያ በመላክ ተጠሪ በ1976 ዓ.ም በካርታ ከያዙት 455 ካ.ሜ ይዞታ ዉጪ አስፋፍተዉ የያዙት ይዞታ መኖር አለመኖሩ ተጣርቶ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ተስጥቶ አመልካች ብቻ በሰጠዉ ምላሽ ተጠሪ በካርታ ከያዙት 455 ካ.ሜ ዉጪ 127 ካ.ሜ አስፋፍተዉ የያዙና የመንግስት ቤት በአካል ባይኖርም በGIS እና CIS መረጃ ላይ እንደነበረ ያሳያል የሚል ምላሽ በመስጠቱ የመንግስት ቤት በበላይነት የማስተዳደር

ኃላፊነት የተሰጣቸዉ የክ/ከተማዉ እና የወረዳ 6 ቤቶች ልማት አስተዳደር ጽ/ቤቶች ጉዳዩ ላይ ምላሽ ለመስጠት እንዳልፈለጉ ግምት በመወሰድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 199(1) መሰረት ምላሽ የመስጠት መብታቸዉን በማለፍ መርምሮ፡- ተጠሪ በካርታ ቁጥር 22091 የቤት ቁጥር 1963 ስፋቱ 455 ካ.ሜ የሆነ ይዞታ አስመልክቶ በነባሩ ካርታ ላይ ባለዉ ልክ በአዲሱ አሠራር አመልካች በአዲስ ካርታ አዘጋጅቶ እንዳይሰጥ የሚያስችለዉ ሕጋዊና ምክንያትዊ መነሻ ሳይኖረዉ ኃላፊነትና ተግባሩን ያለመወጣቱ አግባብነት ያለዉ ሆኖ አልተገኘም በማለት አመልካች ነባሩን ካርታ በአዲስ ካርታ ሰርቶ ለተጠሪ እንዲሰጥ ወስኗል፡፡ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ቅሬታዉን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ግራ ቀኙን አከራክሮ የስር ፍ/ቤቱን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ በመቀጠል ለከተማዉ አስተዳደር ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም የተፈጸመዉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ሊታረም ይገባል በሚል ነዉ፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘት፡- የስር ፍ/ቤት በተከራካሪዎች መካከል ለነበረዉ ክርክር ከሚመለከተዉ አካል ምላሽ አስቀርቦ እና አጣርቶ ዉሳኔ መስጠት ሲገባዉ፤ ትዕዛዝ ከተሰጣቸዉ ሁለቱ ምላሽ ባልሰጡበት በድጋሚ ትዕዛዝ ሊሰጥ እየተገባ፤ ከአንድ ተቋም ቢሆንም የቀረበዉ ምላሽ ተጠሪ ከይዞታቸዉ ዉጭ በአካል መያዛቸዉ ተረጋግጦ ባለበት ከተጠሪ ይዞታ የመንግስት ይዞታ ተለይቶ በይዞታቸዉ መጠን ካርታዉ እንዲሰጣቸዉ መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲሻር የሚጠይቅ ነዉ፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ተጠሪ በ1976 ዓ.ም በ455 ካ.ሜ ላይ የተሰጣቸዉ ካርታ በአዲስ ካርታ ይቀይርልኝ ብለዉ ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት አመልካች ተጠሪዉ የሌላ ሰዉ ቤት እና ይዞታ ጭምር አስፋፍተዉ ስለያዙ የድሮዉን ካርታ መልሰዉ ተነጻጻሪ ካርታ ከሚሰጣቸዉ በቀር ልሰጥ አልችልም፤ ጉዳዩም በአስተዳደር የሚታይ እንጂ በፍ/ቤት የሚታይ አይደለም በሚል አመልካች ያቀረበዉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ጥያቄ በማለፍ እና ፍ/ቤቱም ተጠሪዉ የሌላ ሰዉ ይዞታ እና ቤት ሁሉ አካቶ ስለመያዝ አለመያዙ ተጣርቶ እንዲቀርብለት ለአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቤቶች ልማት አስተዳደር ጽ/ቤት፤ ለክ/ከተማዉ ወረዳ 6 ቤቶች ልማት አስተዳደር ጽ/ቤት እና ለክ/ከተማዉ መሬት ልማት አስተዳደር ጽ/ቤት ትዕዛዝ ከሰጠ በኃላ ዉጤቱን ሳይጠብቅ የሠበር አመልካች ያቀረበዉን መግለጫ ብቻ ተቀብሎ የሁለቱን አስተዳደር አካላት ሪፖርት ሳይቀበል በማለፍ በሰበር ተጠሪዉ የዳኝነት ጥያቄ መሠረት ካርታ በአዲስ ተቀይሮ ሊሰጥ ይገባል ሲል መወሰኑ እና የከተማዉ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤትም ግራ ቀኙ አከራክሮ ማጽናቱ እና የከተማዉ ሰበር ችሎትም ይህንኑ ተቀብሎ በትዕዛዝ ማጽናቱ ተገቢ መሆን አለመሆኑን በሰ/መ/ቁ 31906 እና 72980 ከተሰጠዉ ገዥ ትርጉም አንጻር ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በሰበር ችሎት እንዲታይ የተደረገ ነዉ፡፡

የተጠሪ ወራሾች የሰጡት መልስ ይዘት በአጭሩ፡- በአዋጅ ቁጥር 361/98 አንቀጽ 41(1/ሀ እና ለ) የከተማዉ አስተዳደር ፍ/ቤቶች በይዞታ ጥያቄ ላይ የሚነሱ ክርክሮችንና ከዚሁ ጋር ተያያዥነት ያላቸዉን ጥያቄዎች የማስተናገድ ስልጣን ያላቸዉ በመሆኑና ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 91216 በሰጠዉ ገዥ ትርጉም የተሰጠበት በመሆኑ የስር ፍ/ቤት የአመልካችን መቃወሚያ ዉድቅ ማድረጉ ተገቢ ነዉ፡፡ የስር ፍ/ቤት ሦስቱ የአስተዳደር አካላት አጣርተዉ ምላሽ እንዲሰጡ በተሰጠዉ ትዕዛዝ ምላሽ ባለማቅረባቸዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ 199(1) መሰረት ምላሽ የመስጠት መብታቸዉ መታለፉ ተገቢ ነዉ፡፡ የወረዳዉ ቤቶች ልማት ጽ/ቤት ምላሽ ያላቀረበ ቢሆንም በመ/ቁ 55820 የተጠሪ አዉራሾች በይዞታዉ ዉስጥ የቀበሌ ቤት አለመኖሩ ተረጋግጦ ዉሳኔ የተሰጠበት ነዉ፡፡ ስለሆነም የስር ፍ/ቤቶች በማስረጃ አረጋግጠዉ የሰጡት ዉሳኔ በመሆኑና የተጠሪ ወራሾች ንብረት የማፍራት ሕገ-መንግስታዊ መብት ያገናዘበ በመሆኑ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ዉድቅ እንዲደረግ በመጠየቅ ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን እኛም አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡ የሰበር አቤቱታዉን መርምረን እንደተረዳነዉ ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አንጻር የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሻዉ ጭብጥ፡- ክርክር ባስነሳዉ ይዞታ ላይ የመንግስት ቤት መኖር አለመኖሩን አጣርተዉ ምላሽ እንዲሰጡ ከታዘዙት ሦስት አካላት መካከል የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቤቶች ልማት አስተዳደር ጽ/ቤት እና የክ/ከተማዉ ወረዳ 6 ቤቶች ልማት አስተዳደር ጽ/ቤት ምላሽ ባልሰጡበት ሁኔታ ታልፎ በስር ፍ/ቤት ዉሳኔ መሰጠቱ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 31906 እና 72980 ከሰጠዉ ገዥ ትርጉም አንጻር ተገቢ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነዉ፡፡

በተሻሻለዉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41(1/ሀ እና ለ) የከተማዉ መሪ ፕላን አፈጻጸም የይዞታ ባለመብትነት፣ የፈቃድ አሰጣጥ ወይም የቦታ አጠቃቀምን በተመለከተ የሚነሱ ጉዳዮች፣ ከከተማዉ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላት የመቆጣጠር ስልጣንና ተግባር ጋር በተያያዘ የሚነሱ የፍትሐብሔር ክርክሮችን ተመልክቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ለከተማዉ አስተዳደሩ ፍ/ቤቶች የተሰጠ የዳኝነት ስልጣን መሆኑ ተደንግጓል፡፡ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ያቀረበዉ የዳኝነት ጥያቄ ነባሩ ካርታ በአዲስ ካርታ ተለዉጦ እንዲሰጣቸዉ ቢሆንም አመልካች ካርታ ለመስጠት ፍቃደኛ ያልሆነበት ምክንያት እና ተጠሪ ጉዳዩን ለፍ/ቤት ለማቅረብ የተገደደዉ በተጠሪ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ዉስጥ የመንግስት ቤት መኖር አለመኖሩ በማከራከሩ እንጂ በአዋጅ ቁጥር 1183/12 አንቀጽ 50(2) እና በአዋጁ ክፍል ሦስት የተደነገጉት መርሆች የጣሰ ዉሳኔ በመስጠቱ አይደለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የዳኝነት ስረ-ነገር ስልጣን አስመልክቶ በተከራካሪ ወገን ባይነሳም ፍ/ቤት በራሱ ማንሳት የሚችል ቢሆንም አመልካች በስር

ፍ/ቤት የዳኝነት ስልጣንን አስመልክቶ በተሰጠዉ ብይን ላይ ያቀረበዉ የሰበር አቤቱታ የቅሬታ ነጥብ የለም፡፡ ስለሆነም የስር ፍ/ቤት የዳኝነት ስልጣን ሳይኖረዉ ጉዳዩን ተመልክቶ ወስኗል የሚያስብል አይደለም፡፡

በጭብጥነት ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ አመልካች የተጠሪን ካርታ በአዲስ ካርታ ላለመስጠት የሰጠዉ ምክንያት ለተጠሪ በ1976 ዓ.ም የተሰጠዉ ካርታ ዉስጥ ያለአግባብ የተካተተ የቀበሌ ቤት የሆነ የቤት ቁጥር 346 ወ/ሮ ሊኬ ዳመሳ የሚባሉ ግለሰብ ተከራይተዉት የነበረ ስለመሆኑ በወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ መረጃ ላይ ተመዝግቦ የሚገኝ በመሆኑ እና በGIS እና CIS መረጃ ቋት ዉስጥ የሚያሳይ በመሆኑ በተነጻጻሪ እንጂ በቀጥታ አዲስ ካርታ ለዉጦ ሊሰጥ እንደማይችል በመከራከሩ ምክንያት የስር ፍ/ቤት ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት ይረዳዉ ዘንድ የከተማ አስተዳደሩን የቀበሌ ቤትን ለማስተዳደር ኃላፊነትና ስልጣን የተሰጣቸዉ የክ/ከተማዉ እና የወረዳ 6 ቤቶች ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤቶች ከአመልካች ጋር በመሆን አጣርተዉ እንዲገልጹ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በተጠሪ ካርታ በተገለጸዉ ይዞታ ዉስጥ የመንግስት ቤት በአካል የማይገኝ መሆኑን፤ ሆኖም በGIS እና CIS መረጃ ላይ ቤት የነበረ መሆኑን የሚያሳይ መሆኑንና ተጠሪ አስፋፍቶ የያዘዉ ይዞታ መኖሩን አረጋግጧል፡፡ ሌሎቹ የክ/ከተማዉ እና የወረዳ 6 ቤቶች ልማት አስተዳደር ጽ/ቤቶች ምላሽ ያላቀረቡ በመሆኑ ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 199(1) መሰረት አልፎታል፡፡ አመልካች ራሱ አጣርቶ በተጠሪ ይዞታ ዉስጥ በአካል የመንግስት ቤት አለመኖሩን ያረጋገጠ በመሆኑ የመንግስት ቤትን ለማስተዳደር ኃላፊነት የተሰጣቸዉና ማጣራት ሂደቱ ላይ እንዲሳተፉ በፍ/ቤቱ ዕድል የተሰጣቸዉ ሁለቱ አካላት ምላሽ ያለመስጠታቸዉ መሠረታዊ ለዉጥ የሚያመጣ ባለመሆኑ ጭምር የስር ፍ/ቤት በድጋሚ ትዕዛዝ አለመስጠቱ የሚነቀፍ አይሆንም፡፡

በሌላ በኩል በ1976 ዓ.ም ለተጠሪ በይዞታ ማረጋገጫ ተረጋግጦ በተሰጠ ይዞታ ዉስጥ የመንግስት ቤት በአካል አለመኖሩ በመረጋገጡ የተጠሪን ነባር ካርታ በአዲስ ቀይሮ ላለመስጠት በGIS እና CIS መረጃ ቋት ዉስጥ የመንግስት ቤት የነበረ መሆኑን ሚያመላክት መረጃ መኖሩ ብቻዉን በቂ ባለመሆኑ እንዲሁም ሌላ የሚጣራ ነገር ባለመኖሩ የስር ፍ/ቤት ሁለቱ የቤቶች ልማት ጽ/ቤቶችን አስገድዶ አጣርቶ እንዲያቀርቡ ሳያደርግ ዉሳኔ መስጠቱ ለዉሳኔዉ አሰጣጥ የጠራ ፍሬ ነገር ሳይኖርና ሳይጣራ ዉሳኔ ሰጠ የሚያስብል ባለመሆኑ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 31906 እና 72980 የሰጠዉን ገዥ ትርጉም የሚቃረን ዉሳኔ የስር ፍ/ቤት ሰጥቷል ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች ተጠሪ በካ/ቁጥር 22091 የቤት ቁጥር 1963 የቦታ ስፋቱ 455 ካ.ሜ በሆነዉ ላይ ተሰጥቶት የነበረዉን ነባሩን ካርታ በአዲሱ አሠራር አዲስ ካርታ ሰርቶ እንዲሰጥ የሰጡት ዉሳኔ የሚቀፍበት በቂ ምክንያት አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል በየደረጃዉ ያሉት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ የሚነቀፍበት በቂ ምክንያት ባለመኖሩ ዉሳኔዉ በፌዴራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4) እና 10(1) አንጻር መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ**

1. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 36004/14 ታሕሳስ 14 ቀን 2015 ዓ.ም ተሰጥቶ በአስተዳደሩ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ 39437 የካቲት 29 ቀን 2015 ዓ.ም በተሰጠ ዉሳኔ እና በአስተዳደሩ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 40649 ሚያዚያ 26 ቀን 2015 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ የጸናዉ ዉሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1/ሀ) መሠረት ጸንቷል፡፡
2. ግራ ቀኙ በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

ፋ/ዘ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 251700

ጥር 26 ቀን 2017ዓ/ም

ዳኞች ፦ገበየሁ ፈለቀ

ደረጀ አያና

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

ብርሃኑ መንግሥቱ

አመልካች፦ ደጀኔ ደበላ አልቀረበም ፦ አልቀረቡም

ተጠሪ፦ ኦሮሚያ ጠቅላይ ዐቃቢ ህግ ፦ አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ ይለፍ ወረቀት ሳይይዙ የግብርና ምርቶችን ማጓጓዝ ወንጀል የሚመለከት ነው፡፡ክርክሩ የተጀመረው በሰሜን ሸዋ ዞን ወራ ጃርሶ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡በተጠሪ የቀረበውም ክስ አመልካች የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ያወጣውን የገበያ ቁጥጥርና የምርት ጥራት አዋጅ ቁጥር 234/2013 አንቀፅ 26(3) እና 5 በመተላለፍ ታህሳስ 03 ቀን 2015 ዓ.ም ከቀኑ በግምት 4፡00 ሰአት በወራ ጃርሶ ወረዳ ቀሬ ጎሃ ከተማ ቀበሌ 02 ልዩ ቦታው ኬላ ተብሎ በሚጠራዉ ቦታ የሰሌዳ ቁጥር 3-16932 ኢት በሆነ ሲኖ ትራክ ተሽከርካሪ ላይ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

220(ሁለት መቶ ሃያ) ኩንታል ባቄላ ግምቱ 836,000 (ስምንት መቶ ሰላሳ ስድስት ሺህ) የሆነውን ከአዲስ አበባ ወደ አማራ ክልል አቅጣጫ በመጓዝ ላይ እያለ ከላይ በተጠቀሰው ቦታ ሲደርስ በኬላ ተቆጣጣሪዎች ሲፈተሽ የንግድ ፍቃዱና የመነሻ እና መድረሻ የይለፍ ወረቀት ሳይይዝ በመጓዙ ያለ ፍቃድ የግብር ምርቶችን በማጓጓዝ ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

የአሁን አመልካችም ወንጀሉን አልፈጸምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ክሱን በመካድ የተከራከረ ሲሆን ፍ/ቤቱም በአመልካች እና በተጠሪ የቀረቡትን ምስክሮች በመስማት እንዲሁም የቀረቡትን ሰነድ ማስረጃ መሠረት በማድረግ አመልካች የጥሬ እህል ንግድ ፈቃድ ያለው መሆኑ ቢረጋገጥም እንደ የይለፍ ማረጋገጫ ወረቀት፤ የግዢና ሽያጭ ደረሰኝ፤የክፍያ ደረሰኝ ሳይይዝ የባቄላ ምርት ሲያጓጓዝ የነበረ መሆኑ የተረጋገጠ ስለሆነ በአዋጅ ቁጥር 234/2013 አንቀጽ 26(5) ሥር ጥፋተኛ ነው በሚል በስድስት ወር ቀላል እስራት እና በብር 4000.00 (አራት ሺ) እንዲቀጣ በመወሰን የእስራት ቅጣቱን ለሁለት አመት ተገድቦ እንዲቆይ እንደዚሁም ሲጓጓዝ የተያዘው የባቄላ እህል እንዲወረስ ሲል ወስኗል፡፡

አመልካች በውሳኔው ቅር በመሰኘት ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን በማከራከር አመልካች በተያዙ ጊዜ የንግድ ፈቃድ ይዘው እንደነበረ መረጋገጡን፤ይህ ፈቃድ ያለው ሰው ጥሬ እህልና አገዳ እህል ለመነገድ የተፈቀደለት ስለመሆኑ የሚያስረዳ ከመሆኑም በተጨማሪ የአመልካች እህል የተጫነበት አርሲ ዞን ከእህል ንግድ ጋር በተያያዘ የይለፍ ደብዳቤ ስራ ላይ እንዲውል የተባለው ታህሳስ 03 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ቢሆንም በወቅቱ እንደዚህ ያለውን ፈቃድ የሚሰጥ አካል የሌለ መሆኑ እና እህሉ ደግሞ ከዚያ በፊት የተገዛ እና በመንገድ ላይ የቆየ ስለመሆኑ መረጋገጡን በመጥቀስ የሥር ወረዳ ፍ/ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በመሻር አመልካች በነጻ እንዲሰናበቱ እና የተወረሰው ንብረት እንዲመለስላቸው ወስኗል፡፡

ተጠሪም በተሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታቸውን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ጉዳዩ በይግባኝ ቀረበለት የኦሮሚያ ጠቅላይ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትም አመልካችን በማስቀረብ ካከረካረ በኃላ በሰጠው ውሳኔ አመልካች የንግድ ፈቃድ አለኝ በማለት የተከራከሩ እና ማስረጃ ያቀረቡ ቢሆንም ያቀረቡት የንግድ ፈቃድ ኮድ 61211 ለብዕር እህልና አገዳ እህል የሚሰጥ እንደሆነ፤በኦሮሚኛ በተጻፈበት ቦታ ኮድ 61211 የሚል ሆኖ ከኮዱ በመቀጠል የተጻፈው ቃል የጥሬ እህልና አገዳ ጅምላ ንግድ ተብሎ የተጻፈ መሆኑን፤ይህ

የሚጣጣም መሆኑን የሚያሳይ ቢሆንም የንግድ ሚኒስቴር ያወጣው መመሪያ ላይ ኮድ 61211 ስር የንግድ ፈቃድ መስጠት ያለበት ለብዕር እህልና አገዳ ብቻ መሆኑን፤በዚህም ምክንያት አመልካች እንደ ማስረጃ ያቀረቡት ፈቃድ ጸንቶ ያለ ነው ተብሎ የሚወሰድ አለመሆኑን፤ ለጥሬ እህል ንግድ የሚሰጠው ኮድ 61213 በሚል እንደሆነ፤እንዲሁም አመልካች ማስረጃዎቹን ያቀረቡት ክስ ከቀረበባቸው በኂላ በመሆኑ በህግ ተቀባይነት ያለው አለመሆኑን በመጥቀስ በሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የወረዳ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔን አፅንቷል፡፡

አመልካችም በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ቅሬታቸዉን በሰበር ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ቢሆንም ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

የሰበር አቤቱታዉ ቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ላይ ሲሆን የአቤቱታው ይዘትም በአጭሩ የንግድ ፍቃዱን በተመለከተ በወቅቱ የታየልኝ ሲሆን የተጫነው እህል የይለፍ ወረቀት አለመያዝን በተመለከተ ደግሞ እህሉ የተጫነበት የአርሲ ዞን ዲገሉና ጢጆ ወረዳ ንግድና ገበያ ልማት ፅ/ቤት እህሉ እስከ ተጫነበት ቀን ድረስ አዋጅ ቁጥር 234/2013 በሥራ ላይ ያላዋሉ መሆኑን አሳውቆልኛል፣በተጠቀሰው ተሽከርካሪ ላይ የተጫነው ባቄላ የአቶ ደረጀ ፈዬ ንግድ ፈቃድ በሰሜን ሸዋ ዞን የወራ ጃርሶ ወረዳ ንግድ ፅ/ቤት በተሰጠው የንግድ ፈቃድ ኮድ ላይ ያላቸውን ጥርጣሬ አግባብ እንዳልሆነ በተጫነው እህል ላይ የተያዘው ፍቃድ ትክክል መሆኑን የኦሮሚያ ንግድ ቢሮ በደብዳቤ ገልፆልኛል፣ሰሜን ሸዋ ዞን ንግድ ቢሮም በተዋረድ ለወራ ጃርሶ ወረዳ ንግድ ፅ/ቤት አሳውቆ የተጫነው እህል አመልካች በያዘው የንግድ ፍቃድ ማለፍ እንደሚችልና የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት የእርሻ ውጤቶችና የገበያ ቁጥጥርና የምርት ጥራት አዋጅ 234/2013 አለመታለፉን ተገልፆልኛል፡፡ይህ ሆኖ እያለ አመልካች ወንጀል የመፈፀም ሀሳብ እንደሌለኝ እና የመስሪያ ቤቱ የአሰራር ችግር መሆኑን የሚያሳይ ሆኖ እያለ ወይም በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 23 ስር የተቀመጡትን ጥፋተኛ ሊያስብሉ የሚችሉ መስፈርቶች በአግባቡ ሳይታዩ የተሰጠ ውሳኔ ነው፣የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ጉዳዮች ቋሚ ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና ሰበር ሰሚ ችሎት የአሁን አመልካች ጥፋተኛ ነው ያሉት አመልካች እጅ የተገኘው የንግድ ፈቃድ የአበባ እህልን ወይም ጥራጥሬን አያካትትም ብለዉ ሲሆን ይህ በስር ፍርድ ቤት ያልተነሳ እና ክስም ያልቀረበበት ነዉ፣ማስረጃውም የተሰጠው ወንጀል ከተፈፀመ በኃላ ነው በማለት ይህ ማስረጃ ከሚመለከተው መስሪያ ቤት መቅረቡን እና ማስረጃው ትክክል አለመሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ከድርጊት በኃላ የመከላከያ ማስረጃ የሚሆነውን ማንኛውም ማስረጃ ማቅረብ አይችልም የሚል ህግ በሌለበት ማስረጃውን

ውድቅ በማድረጉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲታረምልኝ የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡

በአመልካች የቀረበው የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በስር ወረዳ ፍርድ ቤትም ሆነ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ጭኖ ለተገኘዉ ባቄላ የጥራጥሬ እህል ንግድ ላይ ለመስራት የሚያስችል ንግድ ፈቃድ ስለመያዙ ተረጋግጦ እያለ እና የወረዳዉ ፍርድ ቤት አመልካችን ጥፋተኛ ያለበት ምክንያት የአመልካች የይለፍ ፈቃድ ያልያዘዉ እህል ጭኖ በተነሳበት ወረዳ ንግድ እና ገበያ ልማት ጽ/ቤት በአዋጁ መሰረት የንግድ ፈቃድ የመስጠት አሰራር ከታህሳስ 4 ቀን 2015 ዓ/ም በፊት ሲሰጥ እንዳልነበር ቢያሳዉቅም አዋጁ በስራ ላይ አስከዋለ ድረስ አመልካችን ከተጠያቂነት አያድንም በሚል ሲሆን የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ደግሞ አመልካች ባቄላ ጭኖ ከተነሳበት ወረዳ የይለፍ ፈቃድ መስጠት አሰራር መተግበር የጀመረዉ ከታህሳስ 03 ቀን 2015 ዓ.ም በኋላ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ ከወንጀል ህጉ አንቀጽ 23(2) ድንጋጌ አንጻር ሲታይ አመልካች ሆን ብሎ እና አስቦ ወንጀሉን ስለመፈጸሙ ስለማያሳይ ጥፋተኛ ሊባል አይገባም የሚል ሆኖ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሁለቱ የስር ፍርድ ቤቶች ያልተነሳዉን እና ተጠሪ ባቀረበዉ የወንጀል ክስ ያልተጠቀሰዉን ምክንያት በመጥቀስ በአመልካች የቀረበዉ ንግድ ፈቃድ ጥሬ እህል የሆኑትን እንደ ባቄላ የመሳሰሉትን ለመነገድ የሚፈቅድ አይደለም በሚል አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት አግባብ መጣራት የሚገባዉ ነዉ በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡

ተጠሪም በአመልካች በቀረበው የሰበር አቤቱታ ላይ በሰጠው መልስ የወረዳው ፍ/ቤት አመልካች ጥፋተኛ ያለበት ምክንያት አመልካች የንግድ ፈቃድ እና የይለፍ ፈቃድ ሳይይዝ እህል ጭኖ ስለተገኘና ይህንኑም በማስረጃ ባለመረጋገጡ እንጂ እህል ከተነሳበት የወረዳ ንግድ ጽ/ቤት በአዋጁ መሰረት የይለፍ ፈቃድ የመስጠት አሰራር ከታህሳስ 03 ቀን 2015 ዓ.ም በፊት መስጠት አልተጀመረም በማለት በደብዳቤ ለወረዳ ፍ/ቤት ስላሳወቀ አይደለም፡፡የኦሮሚያ የመንገድ ይለፍ ወረቀት ክፍያ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 13/2015 አንቀጽ 20 ላይ መመሪያው ከመስከረም 10 ቀን 2015 ጀምሮ ስራ ላይ እንደሚውል የተጠቀሰ ሲሆን አመልካች ግን ያለ ንግድ ፈቃድ እና ያለ ይልፍ ወረቀት የግብርና ምርት የሆነ ባቄላ በማጓጓዝ ወንጀል ተጠርጥሮ የተያዘው ታህሳስ 03 ቀን 2015 ዓ.ም ነው፡፡በዚህ ሁኔታ የአሁን አመልካች የተያዘው የኦሮሚያ የመንገድ ይለፍ ወረቀት ክፍያ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 13/2015 ስራ ላይ ከዋለ በኃላ ሆኖ ሳለ እህል ጭኖ በተነሳበት ወረዳ ንግድ ጽ/ቤት አመልካች የንግድ ፈቃድ እና የይለፍ ፈቃድ ያልያዘበት ምክንያት በአዋጁ መሰረት የይለፍ ፈቃድ የመስጠት አሰራር ከታህሳስ 03 ቀን 2015 ዓ.ም በፊት መስጠት

ስላልተጀመረ ነው መባሉ ተገቢ አይደለም፡፡ስለሆነም የወረዳ ፍ/ቤት እህል ጭኖ ከተነሳበት ወረዳ ንግድ ጽ/ቤት የተጻፈውን ደብዳቤ ውድቅ በማድረግ አመልካች በተጠቀሰው የህግ ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ ናቸው በሚል የተሰጠው የቅጣት ውሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ በአመልካች የቀረበው የሰበር አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክረዋል፡፡

አመልካችም በበኩሉ የሰበር አቤቱዉን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርቦ ክርክሩ ተጠቃሏል፡፡ የክርክሩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተዉን የሚመስል ሲሆን እኛም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር መዝገቡን መርምረናል፡፡እንደመረመርነዉም አመልካች በስር ወረዳ ፍርድ ቤት የቀረበበት ክስ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ያወጣውን የገበያ ቁጥጥርና የምርት ጥራት አዋጅ ቁጥር 234/2013 አንቀፅ 26(3) እና (5) ድንጋጌ በመተላለፍ 220 (ሁለት መቶ ሃያ) ኩንታል ባቄላ ግምቱ 836,000 (ስምንት መቶ ሰላሳ ስድስት ሺህ) የሆነ ከአዲስ አበባ ወደ አማራ ክልል አቅጣጫ በመጓዝ ላይ እያለ በኬላ ተቆጣጣሪዎች የንግድ ፍቃድ እና የመነሻ እና መድረሻ የይለፍ ወረቀት ሳይይዝ ሲያጓጉዝ ተገኝቷል ተብሎ ነዉ፡፡

በመሰረቱ አንድ ሰዉ ወንጀል አደረገ የሚባለው ህገ ወጥነቱ እና አስቀጪነቱ በህግ የተደነገገን ድርጊት ፈጽሞ የተገኘ እንደሆነ ስለመሆኑና አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለውም ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ህጋዊ፣ ግዙፋዊና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ስለመሆኑ በወንጀል ህግ አንቀጽ 23 (1) እና (2) ስር ተደንግጎ የሚገኝ ነው፡፡በወንጀል ጉዳይ የሚቀርብ የክስ ማመልከቻም ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል መሰረታዊ ነገር እና ሁኔታዎች የተገለጹበት፣ ስለወንጀሉ እና ስለሁኔታዉ የሚሰጠዉ ዝርዝር መግለጫ ተከሳሹ ፈጸመ የተባለዉን ተግባር ወንጀል ከሚያደርገዉ ህግ አነጋገር ጋር በጣም የተቀራረበ መሆን እንደሚገባዉ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 111 እና 112 ድንጋጌዎች ላይ ተደነገገዉም ከሳሹን ወገን በ/ወ/ህ/ሕ/ቁ 23(2) ስር የተመለከተዉን የወንጀል ማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮች ተሟልተዉ መገኘታቸዉን ለማስረዳት እንዲያስችለዉ መሆኑን ከድንጋጌዎቹ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በሌላ አነጋገር ከሳሽ ወገን በክሱ መሰረት አስረድቷል ለማለት የሚቻለዉ ቀደም ሲል በተጠቀሱት በወ/መ//ሥ/ሥ/ቁ 111 እና 112 ድንጋጌዎች መሰረት አዘጋጅቶ ባቀረበዉ የክስ ማመልከቻ መሰረት ተከሳሹ ወንጀል መፈጸሙን ማስረዳት በቻለ ጊዜ ስለመሆኑ በሰበር መ/ቁ 91535 እና ተመሳሳይ ውሳኔዎች አስገዳጅ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ በስር ወረዳ ፍርድ ቤትም ሆነ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ጭኖ ለተገኘዉ ባቄላ የጥራጥሬ እህል ንግድ ላይ ለመስራት የሚያስችል ንግድ ፈቃድ ስለመያዙ መረጋገጡ

አላከራከረም፡፡የወረዳዉ ፍርድ ቤት አመልካችን ጥፋተኛ ያለበት ምክንያት አመልካች የይለፍ ፈቃድ ያልያዘዉ እህል ጭኖ በተነሳበት ወረዳ ንግድ እና ገበያ ልማት ጽ/ቤት በአዋጁ መሰረት የንግድ ፈቃድ የመስጠት አሰራር ከታህሳስ 4 ቀን 2015 ዓ/ም በፊት ሲሰጥ እንዳልነበር ቢያሳዉቅም አዋጁ በስራ ላይ እስከዋለ ድረስ አመልካችን ከተጠያቂነት አያድንም በሚል መነሻ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ደግሞ አመልካች ባቄላ ጭኖ ከተነሳበት ወረዳ የይለፍ ፈቃድ መስጠት አሰራር መተግበር የጀመረዉ ከታህሳስ 03 ቀን 2015 ዓ/ም በኋላ ስለመሆኑና አመልካች ሲያንጉዝ የተያዘዉ ታህሳስ 3 ቀን 2015 ዓ/ም እስከሆነ ድረስ ከወንጀል ህጉ አንቀጽ 23(2) ድንጋጌ አንጻር ሲታይ አመልካች ሆን ብሎ እና አስቦ ወንጀሉን መፈጸሙን ስለማያሳይ ጥፋተኛ ሊባል አይገባም ብሎ መወሰኑን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ግን በሁለቱ የስር ፍርድ ቤቶች ያልተነሳዉን እና ተጠሪ ባቀረበዉ የወንጀል ክስ ያልተጠቀሰዉን ምክንያት በመጥቀስ በአመልካች የቀረበዉ ንግድ ፈቃድ ጥሬ እህል የሆኑትን እንደ ባቄላ የመሳሰሉትን ለመነገድ የሚፈቅድ አይደለም በሚል አመልካችን ጥፋተኛ ለማድረግ ተጨማሪ ምክንያት በመውሰድ በወረዳው ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ማጽናቱ ባልቀረበ ክስ ላይ የተሰጠ ዉሳኔ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡የወረዳዉ ፍርድ ቤት አመልካች ባቄላ ለማጓጓዝ ፈቃድ ያለዉ መሆኑ እና የይለፍ ፈቃድ ያልያዘበት ምክንያት ደግሞ በአዋጁ መሰረት የይለፍ ፈቃድ የመስጠት የአሰራር ስርዓት በወረዳዉ ንግድ እና ገበያ ልማት ጽ/ቤት ስላልተጀመረ መሆኑን አረጋግጦ እያለ በወቅቱ አዋጅ ወጥቷል በሚል መነሻ ብቻ አዋጁን የመተግበር ስራ ባልተጀመረበት ሁኔታ እና አመልካች ህጋዊ የንግድ ፈቃድ ይዘዉ እያለ  በቂላ ያለ የይለፍ ፈቃድ ወረቀት ሲያንጉዝ የተገኘዉ ወንጀል ለመፈጸም አስቦ ነዉ የሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰ ስለመሆኑ የሚያሳይ ሲሆን በወቅቱ የይለፍ ፈቃድ የሚሰጥ አካል አልነበረም ተብሎ በተረጋገጠበት ሁኔታ ይህንን የማደራጀትና ፈቃድ የመስጠት የአሰራር ስርዓቱን መዘርጋት እና ስራዉን መተግበር ጉዳዩ የሚመለከተዉ መንግስታዊ አካል ኃላፊነት ሆኖ እያለ አመልካችን የሚመለከት ባልሆነበት ሁኔታ የይለፍ ፈቃድ ሰጪ በሌለበት የይለፍ ፈቃድ አልያዘም በማለት የጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጠበት አግባብ የወንጀል ህግ ቁጥር 23(2) ያላገናዘበ ነው ብለናል፡፡

ሲጠቃለል አመልካች የጥሬ እህል ንግድ የይለፍ ማረጋገጫ ወረቀት ሳይይዝ የባቄላ ምርት ሲያጓጓዝ የነበረ መሆኑ ተረጋግጧል በሚል የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ያወጣውን የገበያ ቁጥጥርና የምርት ጥራት በአዋጅ ቁጥር 234/2013 አንቀጽ 26(5) ስር የተሰጠው የጥፋተኝነት እና ቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የማስረጃ ምዘና መርህ አተገባበር ጉድለት እንደዚሁም በሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጡትን አስገዳጅ ውሳኔዎችን ያላገናዘበ በመሆኑ በፌደራል ፍርድ

ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ቁጥር 2/4(ሸ) እና 10(1)(ሐ) መሰረት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ዉሳኔ

1. በወረ ጃርሶ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 56830 ታህሳስ 24 ቀን 2015 ዓ.ም የተሰጠው የጥፋተኝነት እና ቅጣት ውሳኔ በቅደም ተከተል የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 35008 ሚያዚያ 12 ቀን 2015 ዓ.ም እንደዚሁም በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 431075 ግንቦት 08 ቀን 2015 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ ያጸናው ፍርድ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 9/1(ሀ) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 64721 ጥር 30 ቀን 2015 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢነት ያለዉ ነዉ ተብሎ ጸንቷል ፡፡
3. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

የሰ/መ/ቁ252593

ቀን 27/5/2017

ዳኞች ሺመክት አሰፋ

በእውቀት በላይ

መላኩ ካሳዬ

ማርታ ተካ

አየለ ማሞ

አመልካች፡ መ/ር ምህረት መስፍን ቀረቡ

ተጠሪ፡ አቶ ምስጌ ብርሃን አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች በቀን 10/12/2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 03-121382 በቀን 29/09/2015 ዓ.ም የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አልተፈፀመበትም በማለት በትዕዛዝ በማፅናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡ ጉዳዩ የመፋለም ክስን የሚመለከት ሆኖ ክርክሩ የተጀመረው በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ስማዳ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን በስር ፍርድ ቤት አመልካች ተከሳሽ ተጠሪ ከሳሽ ሆነው ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ በወገዳ ከተማ ቤትኖራ ቀበሌ የሚገኘውን 12 ሜትር በ 14 ሜትር የሆነውን የከተማ ይዞታና ቤት አያታቸው እማሆይ ዘውዲቱ አብተው በምሪት አግኝተው ለልጃቸው ወይም ለተጠሪ እናት ወ/ሮ እባቡ

ማስታወሻ፡ - ይህ የ ሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነ ድ ለ ጥና ትና ምር ምር ሥራ ወይም ለ ግ ን ዛ ቤ እ ን ጂ ለ ፍርድ አ ፈ ጻ ጸ ም ዓ ላ ማ አ ያ ገ ለ ግል ም!

ካሴ በስጦታ የሰጧቸውና ይህንንም ይዞታ የተጠሪ እናት በመሞታቸው ተጠሪ በውርስ ያገኙት ሆኖ እያለ አመልካች በ 2009 ዓ.ም በሀሰት በከተማ ማዘጋጃ ቤት በማስጠናት ይዞታውን የያዙባቸው በመሆኑ ለቀው እንዲያስረክቧቸው እንዲሁም ወጪና ኪሳራ እንዲከፍሏቸው ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች የካቲት 11 ቀን 2012 ዓ.ም የተፃፈ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና አማራጭ መልስ አቅርበዋል፡፡ የአማራጭ መልሳቸውም ይዘት አከራካሪውን ቦታ ጨምሮ 12 ሜትር በ 25 ሜትር የሆነውን ይዞታ ከ 1976 ዓ.ም ጀምሮ ይዘውት እየተገለገሉበት የሚገኝና በ2007 የይዞታ ማረጋገጫ ያወጡበት የራሳቸው ይዞታ በመሆኑ የቀረበው ክስ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራቀኙን ምስክሮች አቅርቦ ከሰማ በኋላ አመልካች አቅርበው ያሰሟቸው ምስክሮች አከራካሪው ይዞታና ቤት የአመልካች ነው ከማለት ውጪ ከ 1975 ዓ.ም ጀምሮ በምሪት ያገኙት ስለመሆኑ አላረጋገጡም እንዲሁም አላስረዱም፡፡ የከተማውን መሬት የሚያስተዳድረው የወገዳ ከተማ አገልግሎት ፍርድ ቤቱ ለሰጠው ትዕዛዝ አመልካች አከራካሪውን ይዞታና ቤት በምን አግባብ እንዳገኙት የሚገልፅ ማስረጃ ባይኖርም ነገር ግን በማህበራዊ ፍርድ ቤት በሸንጎ አስመስክረውና በሰነድ አልባ ኮሚቴ አስጠንተው በቀን 28/07/2007 ዓ.ም ካርታ ተሰጥቷቸዋል ያለ ቢሆንም ተጠሪ ያቀረቧቸው ምስክሮች ይዞታውን የተጠሪ አያት እማሆይ ዘውዲቱ አብተው በ 1975 ዓ.ም የወረዳው ከተማ ከጎሽ ወደ ወገዳ ሲመጣ በምሪት የተሰጣቸው መሆኑንና ይህንንም ለአራት ልጆቻቸው ያከፋፈሉና አሁን ክርክር የተነሳበትን ይዞታ ለአመልካች እናትና ለተጠሪ እናት ያከፋፈሉ ሲሆን አመልካች ለተጠሪ እናት የተሰጠውን ያለአግባብ በመያዝና አካተው ካርታ ያወጡበት ቢሆንም ከአሰራርና ደንብ ውጪ የተገኘ ማስረጃ ሊስተባበል የሚችል መሆኑን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር መዝገብ ቁጥር 27548 ቅፅ 5፣ 7139 ቅፅ 11 እና 67011 ቅፅ 13 አስገዳጅ ውሳኔ የሰጠና ተጠሪ ባቀረቧቸው ምስክሮች ይህን ያተስተባበሉ በመሆኑ 6 ሜትር በ 12 ሜትር የሆነውን ይዞታ ከይዞታው ላይ ቀንሰው አመልካች ለቀው ለተጠሪ ሊያስረክቡ ይገባል እንዲሁም ወጪና ኪሳራ በቁርጥ ብር 1,500 (አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር) ሊከፍሉ ይገባል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ለደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 83262 የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን በማከራከር የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አፅንቶታል፡፡ አመልካች በመቀጠል ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 03-121382 የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ሰበር ሰሚ ችሎቱም የሰበር ቅሬታው አያስቀርብም በማለት ሰርዞታል፡፡ አመልካች አሁን ላይ በዚህ ቅር በመሰኘት ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ነሀሴ 10 ቀን 2015 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ክርክር የተነሳበትን ይዞታ በምን አግባብ እንዳገኙት ተጣርቶ እንዲቀርብ ፍርድ ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት የወገዳ ከተማ መሪ ማዘጋጃ ቤት አመልካች ይዞታውን በማህበራዊ ፍርድ ቤት በሸንጎ አስመስክረውና በሰነድ አልባ ኮሚቴ

አስጠንተው የካርታ ይዞታ ተሰጥቷቸዋል በማለት ምላሽ በሰጠበት ሁኔታ እንዲሁም ያቀረቧቸው የሰው ምስክሮች ክርክር የተነሳበትን ይዞታ ከ 1976 ዓ.ም ጀምሮ ተመርተው የያዙ መሆኑን በአግባቡ መስክረው እያለ፤ የተጠሪ ምስክሮች ግን የሚጋጭ የምስክርነት ቃል በሰጡበትና ተጠሪም ምንም አይነት የሰነድ ማስረጃ አቅርበው ባላስረዱበት ሁኔታ 6 ሜትር በ 12 ሜትር የሆነውን ይዞታ አመልካች ከይዞታው ላይ ቀንሰው ለተጠሪ ለቀው ሊያስረክቡ ይገባል ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊሻርና ወጪና ኪሳራም ሊወሰንልኝ ይገባል በማለት የሰበር አቤቱታቸውን አቅርበዋል።

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የቀረበውን የሰበር አቤቱታ በመመርመር አመልካች ክርክር ያስነሳዉን ይዞታ መጋቢት 28 ቀን 2002 ዓ.ም በማህበራዊ ፍ/ቤት በፍርድ ሸንጎ የራሱ ይዞታ መሆኑን አስመስክሮና ሐምሌ 25 ቀን 2006 ዓ.ም በሰነድ አልባ ኮሚቴ አስጠንቶ 12 በ 25 ካሬ ሜትር የሆነ ይዞታ ላይ መጋቢት 28 ቀን 2007 ዓ.ም የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የተሰጠዉ መሆኑ በወገዳ ከተማ መሪ ማዘጋጃ ቤት ለስር ፍ/ቤት በተሰጠ ምላሽ ተረጋግጦ እያለ የተጠሪ አያት ይዞታዉን ስለመመራታቸዉም ሆነ በሕግ አግባብ በስጦታና በዉርስ ለተጠሪ መተላለፉን የሚያረጋግጥ ሰነድ ባልቀረበበት ሁኔታ ከአመልካች ይዞታ 6 በ 12 ካሬ ሜትር ይዞታ ተቀንሶ ለተጠሪ ለቅቆ እንዲያስረክብ ተብሎ በስር ፍ/ቤቶች መወሰኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 1195፣ 1196፣ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 67011፣ 183001 እና በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ - መንግስት አንቀጽ 40 ንብረት የማፍራትና ያለአግባብ ያለመፈናቀል መብት እንዲሁም ከማስረጃ ምዘና መርህ አንጻር ለማጣራት ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል።

ተጠሪ መጥሪያ የደረሳቸው ቢሆንም መልስ ያላቀረቡ በመሆኑ መልስ የማቅረብ መብታቸው ታልፏል። እኛም የቀረበውን ቅሬታ ፣የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ እና የተያዘውን ጭብት ከተገቢው ህግ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል። አመልካች ክርክር የተነሳበትን መሬት ለረጅም ግዜ ይዘው ሲገለገሉበት እንደነበረ የተረጋገጠ ነው። ይህ እንዳለ ሆኖ በማህበራዊ ፍርድ ቤት ይዞታው በእጃቸው እንደቆየ በማስመስከር በሰነድ አልባ መሬቱን በሚያስተዳድረው አካል ተጠንቶላቸው በ2007 ኢ.ም የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ አግኝተው ይዘውት የሚገኝ ይዞታ ነው። በሌላ በኩል ተጠሪ  አያታቸው ለናታቸው ይህን ቦታ ስለመስጠታቸውም ሆነ፤ አያታቸው ይህን ቦታ በምሪት ስለማግኘታቸው የሚያሳይ ሰነድ የለም። ተጠሪ የሰው ምስክር ቦታው የሁለቱም አያት ነበር ፤የግራቀኙ እናቶች እህትማማች ነበሩ አያታቸው አካፍለው ሰጧቸው በማለት መስከረላቸው ተብሎ ነው የአመልካች የይዞታ ማረጋገጫ ከአሰራርና ከደንብ ውጪ ተገኘ ተብሎ 6×12የሚሆን ቦታ ከአመልካች ተቀንሶ ለተጠሪ እንዲሆን የተወሰነው።

አመልካች ቀደም ብሎ በጃቸው የነበረን ይዞታ በ2007 ኢ.ም የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ያገኙት በሰነድ አልባ አስጠንተው ነው። ይህን ጥናት የሚያጠናው ደግሞ ከተማውን የሚያስተዳድረው አካል ነው። ጥናቱን ያጠናው አካል የሌላ ሰው መሬት ቢሆን አጥንቶ ሊደርስበት ይችላል ተብሎ ይታሰባል። የምስክር ወረቀቱ

ወይም የይዞታ ማረጋገጫ ካርታው በተጭበረበረ መንገድ ተገኘ ለማለት በቂ ምክንያት ያስፈልጋል፡፡የፍ/ህ/ቁ 1196 የምስክር ወረቀቱ የተሰጠው ከደንብ ውጪሲሆን፣ወይም ስልጣን በሌለው አካል ሲሰጥ፣ ወይም በማይረጋ ጽሁፍ ተመስርቶ ሲሰጥ፤ወይም ደግሞ ከሳሽ የማይንቀሳቀስ ንብረት ያገኘው የምስክር ወረቀቱ ከተሰጠ በኋላ ከሆነ ነው የምስክር ወረቀቱ ተቀባይነት እንደማይኖረው ያስቀመጠው፡፡ ወደተያዘው ጉዳይ ስንመጣ ግን ይህን የሚያሳይ ምንም ነገር የለም፡፡ ይልቁንም አመልካች አጥንቶ ለሚሰጠው አካል አቅርበው በሰነድ አልባ ተጠንቶ ነው ካርታው የሰጣቸው፡፡

የሰበር መ/ቁ67011 የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነትን አስመልክቶ የሚሰጥ የባለቤትነት ማረጋገጫ ወረቀት ተገቢውን ስርአትና ደንብ በመከተል መሰጠት የሚገባው ስለመሆኑ የሚገልጽ ነው፡፡ ለአመልካች የተሰጣቸው ደግሞ ተገቢ ስርአትና ደንብ ተከትሎና በሰነድ አልባ ተጠንቶ ስለመሆኑ መዝገቡ ስለሚያሳይ ተገቢ ባልሆነ መንገድ አገኙት የሚባል ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም በክልሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ውሳኔ**

- የስማዳ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 14704 በየካቲት 28/2014 የወሰነውንና የደ/ጎ/ከ/ፍርድ ቤት በመ/ቁ83262 በህዳር19/2015፤ እንዲሁም የአ/ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 121382 በግንቦት 29/2015 ያጸኑትን ውሳኔ በሰበር/ስ/ስ/መመርያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1)(ለ) መሰረት ሽረን የክርክሩ ቦታ የአመልካች ነው ብለን ወስነናል፡፡
- የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 252875

ጥር 27 2017ዓ/ም

ዳኞች፡-ገበየሁ ፈለቀ
ደረጀ አያና
ደጀኔ አያንሳ
ኑረዲን ከድር
ብርሃኑ መንግሥቱ

አመልካቾች፡- 1ኛ. አቶ ሽፈራው ሰለሞን
2ኛ. አቶ ሽመክት ሰለሞን
3ኛ. አቶ መካሻ ሰለሞን
4ኛ. አቶ ታረቀኝ ሰለሞን — vc አይሰራም
5ኛ. ወ/ሮ አለሚ ሰለሞን

ተጠሪ፡- ወ/ሮ እየሩሳሌም ሐይላይ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የስጦታ ውል ይፍረስልን ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክሱ በቀረበበት በሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካቾች ከሳሽ፤ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ አመልካቾች ያቀረቡት ክስም በአጭሩ፡- የአመልካቾች አያት የሆኑት ሟች ወ/ሮ ሐረግ ተሰማ በሐረር ከተማ ሸንኮር ወረዳ ቀበሌ 10 የቤት ቁጥር 589 የሆነው ቤት ውስጥ ሲኖሩ ቆይተው በ2010 ዓ.ም ከዚህ አለም በሞት መለየታቸውን ገልጸው የውርስ ሀብት በሆነው መኖሪያ ቤት ላይ በ2003 ዓ.ም ያደረጉት ስጦታ ውል እንዲፈርስ በሚል ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መልስ አመልካቾች ክስ ያቀረቡበት ቤት ቀደም ብሎ በሐረሪ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 48349 የውርስ ሀብት አይደለም ተብሎ ውሳኔ የተሰጠበት ስለሆን በድጋሚ ክስ ሊቀርብበት አይችልም፤ለክሱ ምክንያት የሆነው ቤት የውርስ አካል አለመሆኑ ተረጋግጦ ክሱ ውድቅ በመሆኑ፤እንዲሁም ከተራ ቁጥር 2 እስከ 5 ያሉ አመልካቾች ወራሽ ስለመሆናቸው ሳያረጋግጡ

ያቀረቡት ክስ የክስ ምክንያት የሌለው መሆኑን፤ክስ የቀረበበትን ቤት በታህሳስ 11 ቀን 2003 ዓ.ም ሟች ለተጠሪ በስጦታ ካስተላለፉ ከ11 አመት በኋላ እንዲሁም አውራሽ የሆኑት ወ/ሮ ሐረን ተሰማ ከሞቱ አራት አመት በኋላ የቀረበው ክስ በይርጋ የታገደ ነው፤ ክሱ የቀረበለት የሐረሪ ክልል ህዝብ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም የሚሉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድም ክርክራቸውን አቅርበዋል፡፡

አመልካቾች በተጠሪ በኩል ለተነሱት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ላይ በሰጡት መልስ በአከራካሪው ቤት ላይ ተደርጓ የተባለውን የስጦታ ውል አስመልክቶ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ክስ ማቅረብ እንደሚቻል በመዝገብ ቁጥር 48349 ላይ ውሳኔ ስለተሰጠ ክሱ በዲጋሚ የቀረበ አለመሆኑን፤ያለ አግባብ ወራሾችን በመንቀል የተደረገ የሥጦታ ስምምነትን በመቃወም የቀረበው ክስም የክስ ምክንያት ያለው መሆኑን፤በመዝገብ ቁጥር 48349 ላይ ሲከራካሩ ቆይተው በ2013 ዓ.ም ውሳኔ መሰጠቱ ይርጋውን የሚያቋርጠው መሆኑንና አከራካሪው ቤት በከተማው ክልል ውስጥ ስለሚገኝ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ሥልጣን ስላለው የቀረበው መቃወሚያ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራካረዋል፡፡

የሐረሪ ሕዝብ ክልል መንግስት ከፍተኛ ፍርድ ቤትም መቃወሚያውን መርምሮ ግንቦት 30 ቀን 2014 ዓ.ም በሰጠው ብይን ለክርክር መነሻ የሆነውን ቤት በተመለከተ 1ኛ አመልካች፤ተጠሪ እና ወ/ሮ አለም ስጦቴ በተባሉ ግለሰብ መካከል በመዝገብ ቁጥር 48349 በተደረገው የውርስ ማጣራት ክርክር በሐረሪ ከተማ ቀበሌ 10 ውስጥ የሚገኘው የቤት ቁጥር 589 በስጦታ መተላለፉን የሚያመለክት ማስረጃ ስለቀረበ የውርስ ሀብት የሚያሰኝ ነገር አልተገኘም በሚል በ1ኛ አመልካች በኩል የተጠየቀው ዳኝነት የታለፈ ከመሆኑም በተጨማሪ ስጦታ ይፍረስልኝ የሚለው ጥያቄም በዚሁ መዝገብ ላይ ተጣቃሎ መቅረብ ስለነበረበት አመልካቾች አስቀድሞ የመጨረሻ ውሳኔ ባገኘ ጉዳይ ላይ ዳግመኛ ክስ ማቅረብ የማይችሉ መሆኑን፤አስቀድሞ በ1ኛ አመልካች እና በተጠሪ መካከል ክርክር መደረጉ በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 1851(ለ) መሠረት ይርጋውን የሚያቋርጠው መሆኑን፤መብትና ጥቅምን በተመለከተ ከ2ኛ እስከ 5ኛ ድረስ ያሉ አመልካቾች የውርስ ሀብቱ ላይ ከህግ የመነጨ መብትና ጥቅም ያላቸው ስለመሆኑ ሳያረጋግጡ ያቀረቡት ክስ መሆኑን ፍርድ ቤቱ የተገነዘበው ቢሆንም ይህ መቃወሚያ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 244/2 መሰረት በመቃወሚያነት የሚቀርብ አይደለም በሚል አልፎ የመጨረሻ ውሳኔ ባገኘ ጉዳይ ላይ አመልካቾች ክስ ማቅረብ አይችሉም በማለት በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 245/2 መሰረት መዝገቡን ዘግቷል፡፡ አመልካቾች በዚህ ብይን ቅር ተሰኝተው ያቀረቡት የይግባኝ አቤቱታ በይግባኝ ሰሚው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 337 መሰረት መሰረዙን ተከትሎ አመልካቾች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ጉዳዩን የተመለከተው የሐረሪ ሕዝብ ክልል መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚው ችሎት የሐረሪ ሕዝብ ክልል መንግስት ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካቾችን ክስ ውድቅ ያደረገው በፍትሐ

ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 5 መሰረት ቢሆንም አመልካቾች ለተጠሪ ተደርጎላታል የተባለው የስጦታ ውል እንዲፈርስ ያቀረቡት ክስ በይርጋ የሚታገድ ሆኖ ስላገኘን የሥር ፍርድ ቤት ጉዳዩን የዘጋበት አካሄድ የተለየ ቢሆንም በውጤት ደረጃ ልዩነት አያመጣም በሚል የሐረሪ ሕዝብ ክልል መንግስት ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 348/1 መሠረት አጽንቷል፡፡

የሰበር ቅሬታ የቀረበው በየደረጃው ያሉ ጉዳዩን የተመለከቱት የሐረሪ ሕዝብ ክልል መንግስት ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት በሰበር ለማሳረም ሆኖ የሰበር ቅሬታው በአጭሩ፡- 1ኛ አመልካች በመዝገብ ቁጥር 47485፤እንዲሁም ከ2ኛ-5ኛ ድረስ ያለት አመልካቾች ደግሞ በመዝገብ ቁጥር 53951 የሟች አያታቸው ምትክ ወራሽነት በማረጋገጥ በመዝገብ ቁጥር 48349 የሟች አያታቸው ውርስ ተጣርቶ ድርሻቸውን ለመከፋፈል ባቀረቡት ክስ ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት በስጦታ ተላልፎልኝ ስመ ሀብቱም በስሜ የዞረ ነው የሚል ክርክር እና ማስረጃ ስላቀረቡ ፍርድ ቤቱ በቤት ቁጥር 589 ላይ የተነሳው ክርክር ከውርስ ማጣራቱ ጋር አልታየም በሚል ስላለፈው የስጦታ ውሉ መፍረስ አለበት የለበትም የሚል ጭብጥ ይዞ የሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ በሌለበት፤የስጦታ ይፍረስልን ዳኝነት ባልተጠየቀበት፤ውርስ ተጣርቶ የድርሻ ክፍፍል ይደረግ የሚለው የዳኝነት ጥያቄ ከስጦታ ይፍረስልን የዳኝነት ጥያቄ ጋር የሚያመሳስላቸው ነጥብ በሌለበት የስጦታ ይፍረስልን ክሱ በድጋሚ የቀረበ ነው በሚል መዝገቡ መዝጋቱ እና በየደረጃው ያሉ ፍርድ ቤቶችም ይህን ሳያርሙ ማለፋቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት በአመልካቾች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ የስጦታ ይፍረስልን ክስ የመጨረሻ ውሳኔ ያላረፈት ጉዳይ መሆኑንና የስጦታ ውሉ እንዲፈርስላቸው መብትና ጥቅም ያላቸው መሆኑን የሚመለከት ሆኖእያለ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የይርጋ ጉዳይ የቅሬታቸው አካል ባልሆነበት እና ዳኝነት ባልጠየቁበት ጉዳይ በደፈናው አመልካቾች አቅርበውት የነበረው ክስ በይርጋ የታገደ ነው በማለት አቤቱታቸውን ውደቅ ማድረጉ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉን ቁጥር 182/1 ድንጋጌን የጣሰና የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን፤ የስጦታ ውሉ አመልካቾችን ሙሉ በሙሉ ከውርስ የነቀለ በመሆኑ፤እንዲሁም ሟች የአመልካቾች አያት ዕድሜያቸው ከ85 ዓመት በላይ የሆናቸው በእርጅና ምክንያት የጃጁ፤ማንበብና መፃፍ በማይችሉበት ሁኔታ ውስጥ ሆነው ታህሳስ 11 ቀን 2003 ዓ.ም ያደረጉት ስጦታ ውል እንዲፈርስ የቀረበውን ጥያቄ የሥር ፍርድ ቤቶቹ ውደቅ ማድረጋቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን ጠቅሰው በየደረጃው ያሉት ጉዳዩን የተመለከቱት ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡

በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 6/1 መሠረት ለሰበር ሰሚው ችሎቱ የተመራው የሰበር አቤቱታ በሰበር ሰሚ ችሎቱ ተመርምሮ ተጠሪ ያቀረቡት የይርጋ መቃወሚያ 1ኛ አመልካች በተጠሪ ላይ ያቀረቡትን ክስ መሠረት አድርጎ የይርጋው አቆጣጠር

በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 1851(ለ) መሠረት የተቋረጠ መሆኑን በመጥቀስ የይርጋ መቃወሚያውን ውድቅ አድርጎ እያለ እና ይህ ውሳኔ በይግባኝ ሰሚው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፀንቶ እያለ እና አመልካቾች በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 5 እና 33 መሠረት መዝገቡ መዘጋቱን በመቃወም ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ መሠረት አድርጎ መዝገቡ በይርጋ መዘጋቱ ተገቢ አይደለም በሚል ያቀረቡት የሰበር ቅሬታ በሌለበት አመልካቾች ያቀረቡት ክስ በይርጋ ውድቅ የማድረጉ አግባብነት ሊመረመር ይገባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡ ታዞ በሰጡት መልስ፡- በስር ፍርድ ቤት የስጦታ ውል ይፍረስልኝ አቤቱታው በይርጋ የታገደ መሆኑን ተጠሪ አንስተው ተከራክረው የነበረ ቢሆንም ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣን የተመለከተው የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ካቀረቧቸው መቃወሚያዎች ውስጥ ጉዳዩ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው የሚለውን መርጦ መዝገቡን መዝጋቱን በመቃወም አመልካቾች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ጉዳዩን የተመለከተው የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የስጦታ ይፍረስልኝ ጥያቄው የቀረበው ከ11 አመት በኋላ በመሆኑ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይርጋ መቃወሚያ ቀርቦለት እያለ በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 1845 አንጻር ሳይመረምረው ማለፉ የህግ ስህተት መኖሩን ተረድቶ ማረሙ በህግ የሚደገፍ እንጂ የሚነቀፍ አለመሆኑን ጠቅሰው የአመልካቾች አቤቱታ ውድቅ እንዲሆን ጠይቀዋል፡፡

አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለ መልኩ የተመለከተው የግራ ቀኝ ክርክር እና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ውሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንፃር የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይንም የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል በማቅረብ ፍትሕ ማግኘት መሰረታዊ መብት መሆኑን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 37/1 ይደነግጋል። ፍርድ ቤቶች ይህን መብት የማክበርና የማስከበር ኃላፍነትና ግዴታ እንዳላባቸው ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 13/1 ድንጋጌ መረዳት ይቻላል። ፍትሕ የማግኘት መሠረታዊ መብት ዕውን ሊሆን የሚችለው ፍርድ ቤቶች የተከራካርዎችን ክርክር የመስማት፣ማስረጃቸውን የመቀበል፣ማስረጃ የማስቀረብ፣ማስረጃ የመመርመር፣የመመዘን በአጠቀላይ ክርክሩ የሚመራበትን በሕግ በተዘረጋው ሥርዓት መሠረት ኃላፊነታችውን በአግባቡ ሲወጡ ነው።

በልዩ ሕግ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር የፍትሐ ብሔር ክርክር የሚመራው እና እልባት ማግኘት ያለበት በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ በተዘረጋውን ሥነ ሥርዓት ተከትሎ ነው፡፡ ፍርድ ቤቶች የቀረበላቸውን የጽሑፍም ሆነ የቃል ክርክር የሚመሩበት፣ማስረጃዎችን መዝነው እና መሠረታዊ ህጎችን ተርጉመው ለጉዳዮች እልባት መስጠት ይችሉ ዘንድ ሥርዓት ያስፈልጋቸዋል፡፡ ክርክሮች የሚመሩባቸውን ሥርዓት እና ደንቦች በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ተቀርጸው ስራ ላይ እንዲውሉ

የሚደረግበት ዋናው ምክንያትም ይኼው ነው፡፡ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ የፍትሐ ብሔር ክርክሮችን አስመልክቶ የምንከተለው ስርዓት ሲሆን አጠቃላይ ዓላማውም የፍትሐ ብሔር ክርክሮች ፍትሐዊ፣ኢኮኖሚያዊ እና ቀልጣፋ በሆነ ሁኔታ በመምራት ፍትሐዊ ውሳኔ እንዲያገኙ ማስቻል ነው፡፡ ይህን ዓላማ ለማሳካት ይቻል ዘንድም የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ የተለያዩ ደንቦች እና መርሆዎችን ይደነግጋል፡፡ ክርክሮች በዘፈቀደ ሳይሆን ሥርዓት ባለው ሁኔታ እንዲመሩ በማድረግ የተከራካሪ ወገኖችን የመሰማት መብትን፣ ብሎም ክርክሮች ባነሰ ወጪ እና ጊዜ መቋጫ እንዲያገኙ በማድረግ በፍርድ ቤት እና በተከራካሪ ወገኖች ላይ ያላግባብ የሚደርሰውን የገንዘብ እና የጊዜ ብክነት በማስቀረት የክርክሩ ሂደትም ሆነ ውጤቱ ፍትሐዊ እንዲሆን በማድረግ ረገድ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ የሚኖረው ሚና ከፍተኛ በመሆኑ በህጉ ላይ የተመለከቱትን ደንቦች እና መርሆዎች በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውሉ የማድረጉ አስፈላጊነት የሚያጠያይቅ አይደለም፡፡ በዚህ ረገድ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጋችን ዕውቅና ከተሰጣቸው ደንቦች ውስጥ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊያሳልፉ የሚችሉት ከተጠየቀው ዳኝነት አንጻር ብቻ መሆኑን የሚያመለክተው በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 182፣224/1 እና 226/1 የተመለከተው ድንጋጌ አንዱ ነው፡፡ የሰበር ሰሚ ችሎቱም በሰበር መዝገብ ቁጥር 37761፣37762 (ቅጽ 8 እንደታተመው)፣እንዲሁም በሌሎች በርካታ መዛግብት ላይ አስገዳጅ ውሳኔን ሰጥቷል፡፡

ፍርድ ቤት በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 244 መሠረት በሚቀርቡ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ላይ የሌላውን ተከራካሪ ወገን አስተያየት ተቀብሎ እና ተገቢ ሆኖ ሲገኝም ክርክሩን በማስረጃ አንጥሮ ውሳኔ እንደሚሰጥ ከቁጥር 245(1) ድንጋጌ መረዳት ይቻላል፡፡ ተከራካሪ ወገኖች የሚያቀርቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ላይ ብይን ሳይሰጥ በማለፍ የሚሰጥ ውሳኔ ተገቢነት የሌለው መሆኑን የሰበር ሰሚ ችሎቱ በሰበር መዝገብ ቁጥር 59294 አስገዳጅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ይርጋ የመብት ጥያቄ በህጉ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ባለመቅረቡ በጊዜ ማለፍ ቀሪ የሚሆንበት፣ ተጠያቂነትን በማስቀረት ያልነበረ መብትን የሚያጎናጽፍ ነው። ይርጋ ዳተኛ መብት ጠያቂዎችን መብት የሚያሳጣ በአንፃሩ ባለዕዳው ሁልጊዜ ያለበትን ዕዳ እያሰበ በስጋት እንዳይኖር ነፃ የሚያወጣ ነው። ሕጉ ይህን መብት አንስቶ የመከራከር ዕድል ለባለዕዳው የሰጠ ሆኖ መከራካሪያውን ማንሳት የሚችለው በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መልክ ነው፡፡ የይርጋ መቃወሚያ ተጠቃሚ የሆነ ሰው በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 244 (ሠ) መሠረት በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ለማንሳት መብት ያለው ቢሆንም ይህን መብቱን መተው እንደሚችል የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1856 ያስገነዝበናል። በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ክርክር የይርጋ መከራከሪያ መብቱን ያልተጠቀመ ተከሳሽ መብቱን እንደተወው ስለሚገመት ዳኞች ክርክሩን ማንሳት ስለማይችሉ ፍሬ ነገሩን መርምረው ውሳኔ ይሰጣሉ፡፡ የፍትሐብሔር ሕጉ ቁጥር 1851 ይርጋ የሚቋረጥባቸውን ምክንያቶች ይዘረዝራል፡፡ ይርጋ ከተቋረጠ እንደ አዲስ የሚቆጠር መሆኑን ከቁጥር 1852 ድንጋጌ መረዳት ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች ያቀረቡት ክስ ውሳኔ ባገኘ ጉዳይ ላይ በድጋሚ የቀረበ ነው፤ ከተራ ቁጥር 2 እስከ 5 ያሉ አመልካቾች ወራሽነታቸውን ሳያረጋግጡ ያቀረቡት ክስ የክስ ምክንያት የለውም፤ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት ታህሳስ 11 ቀን 2003 ዓ.ም ሟች በስጦታ ካስተላለፉ ከ11 ዓመታት በኋላ ፤እንዲሁም የአመልካቾች አውራሽ የሆኑት ወ/ሮ ሐረን ተሰማ ከሞቱ አራት አመት በኋላ የቀረበ ክስ በይርጋ የታገደ መሆኑን፤ክሱ የቀረበለት የሐረሪ ክልል ህዝብ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ጉዳዩን የማየት የሥረ-ነገር ስልጣን የለውም በማለት ተጠሪ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን አንስተው የተከራካሩ ሲሆን ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣን የተመለከተው የሐረሪ ክልል ህዝብ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አስቀድሞ በ1ኛ አመልካች እና በተጠሪ መካከል ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን በሐረር ከተማ ሸንኮር ወረዳ ቀበሌ 10 ውስጥ የሚገኝ የቤት ቁጥር 589 ቤት ላይ አስቀድሞ ክርክር መደረጉ በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 1851(ለ) መሠረት ይርጋውን ያቋርጣል በሚል ውድቅ አድርጎ ክሱ የመጨረሻ ውሳኔ ባገኘ ጉዳይ ላይ ዳግም የቀረበ ነው የሚል ብይን ሰጥቷል፡፡ ይህንን ብይን በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካቾች የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታቸው ተቀባይነት ስላላገኘ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎትም ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን የተመለከተው የሐረሪ ክልል ህዝብ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይርጋ መቃወሚያውን ውድቅ ማድረጉ አግባብ አይደለም በሚል ለይግባኝ ሰሚው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የይግባኝ አቤቱታ ቀርቦ ሊታረም ባለመቻሉ የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ በሰበር ሰሚ ችሎቱ ሊታረም ይገባል የሚል አቤቱታ ባልቀረበበት አመልካቾች ያቀረቡት ክስ የመጨረሻ ውሳኔ ባገኘ ጉዳይ ላይ ዳግመኛ የቀረበ ነው ተብሎ ውድቅ መሆኑን አግባብ አይደለም በማለት ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በተጠሪ በኩል የቀረበ መስቀለኛ የሰበር አቤቱታ ሳይኖር አመልካቾች የቀደመው ክርክር የውርስ ማጣራት እንጅ የስጦታ ውል ይፈረስልን የሚል ባለመሆኑ የክርክሮቹ ጭብጥ የተለያየ በመሆኑ ጉዳዩ የመጨረሻ ውሳኔ አግኝቷል መባሉ አግባብ አይደለም በማለት ካቀረቡት ክርክር አንፃር ጉዳዩን ተመልክቶ እልባት መስጠት ሲገባው ያልተጠየቀ ዳኝነትን መሠረት አድርጎ እና ከውጤት አንፃር የሥር ፍርድ ውሳኔ በበላይ ፍርድ ቤት የሚፀናው ለሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ መሠረት ከሆኑት ከአንድ በላይ ምክንያቶች ውስጥ በይግባኝ ወይንም በሰበር ጉዳዩን በሚመለከተው ፍርድ ቤት ከፊሉ ምክንያት መለወጥ አጠቃላይ ውጤቱን የማይለውጠው ሲሆን እንጅ በሥር ፍርድ ተቀባይነት ያጣ የይግባኝ ወይንም የሰበር አቤቱታው ያልቀረበበት ምክንያት ተወስዶ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሊፀና የሚችልበት የሕግ አግባብ በሌለበት ከውጤት አንጻር ጉዳዩን ተመልክቶ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔን ማጽናቱ የሚነቀፍ በመሆኑ ቀጣዩ ተወስኗል፡፡

**ውሳኔ**

1. የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚው ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 00513 ሰኔ 6 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ እና ትዕዛዝ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ- ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 9(1/ለ) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተጠሪ በኩል ከተነሱት በዛ ያሉ መቃወሚያዎች መካከል የመጨረሻ ውሳኔ ባገኘ ጉዳይ ላይ ዳግም ክስ መቅረቡ ተገቢ አይደለም በሚል ውድቅ ማድረጉን በመቃወም አመልካቾች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ መነሻነት ጉዳዩን የተመለከተው የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት በተጠሪ በኩል የቀረበ መስቀለኛ የሰበር አቤቱታ ሳይኖር ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው ማለቱ ሥነ ሥርዓታዊ አይደለም ብለናል፡፡
3. የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት በውሳኔ የዘጋውን መዝገብ ቁጥር 00513 በማንቀሳቀስ አመልካቾች ካቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አንፃር ጉዳዩን ተመልክቶ ተገቢ የሆነውን ህጋዊ ውሳኔ እንዲሰጥ መዝገቡ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 9/2 መሠረት መልሰንለታል፡፡
4. ታህሳስ 2 ቀን 2017 ዓ.ም በመዝገቡ ላይ የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
5. የውሳኔው ትክክለኛ ግልባጭ ለሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት ይድረስ፡፡
6. በዚህ ችሎት የተደረገው ክርክር ላስከተለው ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ውሳኔ አግኝቶ ስለተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት


የሰበር መ/ቁ 253303

ጥር 28 ቀን 2017 ዓ/ም

ዳኞች - ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራዉ

ብርቅነሽ እሱባለዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች --- አቶ ቴዎድሮስ መስፋን ህንፃ ሥራ ተቋራጭ - ጠ/ሀይሉ ታደሰ ቀረቡ

ተጠሪ --- አዲስ አበባ ቤቶች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት (በአሁኑ - የአ/አ ቤ/ልማት ኮርፖሬሽን) - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከለታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ የግንባታ ዉልን የሚመለከት ነዉ፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ አመልካች የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 04664 እና መ/ቁ 06910 አጣምሮ ሰኔ 24 ቀን 2014 ዓ/ም የሰጠዉን ዉሳኔ ፤ የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 37544 ህዳር 28 ቀን 2015 ዓ/ም የሰጠዉን ዉሳኔ ፤ እንዲሁም የአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 40218 ሰኔ 28 ቀን 2015 ዓ/ም የሰጠዉን ዉሳኔ በመቃወም ነው፡፡


ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ተጠሪ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረበው ክስ ከአመልካች ጋር መስከረም 26 ቀን 2008 ዓ/ም ጠቅላላ ዋጋዉ የብር 19,044,907.52 (አስራ ዘጠኝ ሚሊዮን አርባ አራት ሺ ዘጠኝ መቶ ስባት ከ52/100) የህንፃ ግንባታ ዉል የፈፀምን ሲሆን መንግስት ለዜጎች የስራ እድል ከመፍጠር አኳያ በዘርፉ የሚገኙ ተቋራጮች በአንድ ዘርፍ ብቻ እንዲሳተፉ ስለተደረገ አመልካች በአዲስ አበባ አስተዳደር የቁጠባ ቤቶች ኢንተርፕራይዝ ሥር በግንባታ ስራ ያለመሳተፍ ማስረጃ እንዲያቀርብ ተጠይቆ ተጠሪ መስከረም 12 ቀን 2008 ዓ/ም የተፃፈ ሀሰተኛ ማስረጃ በማቅረቡ በዉሉ አንቀፅ 2 መሰረት የማጭበርበር ስራ የፈፀመ በመሆኑ ዉሉ የተቋረጠ ሲሆን አመልካች አለአግባብ የወሰደውን ብር 3,264,297.15 (ሶስት ሚሊዮን ሁለት መቶ ስልሳ አራት ሺ ሁለት መቶ ዘጠና ስባት ከ15/100) ቅድመ ክፍያ ለመመለስ ፍቃደኛ ስላልሆነ ይህን ገንዘብ ከወለድ ጋር እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡

አመልካች በሰጠው መልስ ተጠሪ ባደረገዉ ጥሪ መሰረት ያለን የስራ አፈፃፀምና የፍቃድ ደረጃ ታይቶ ከተጠሪ ጋር የህንፃ ግንባታ ዉል በማድረግ ስራችን የጀመርን እና የሶስት ብሎኮች የቁፋሮ ስራ 20% በላይ ከሰራን በኃላ ተጠሪ አመልካችን ለግዜዉ ከማገድ ያለፈ ዉሉ ስለማቋረጡ ደብዳቤ አልደረሰንም፡፡ ተጠሪ ለዉሉ መቋረጥ ምክንያት ብሎ የጠቀሰዉ ከዋናዉ ስራ ጋር የማይገናኝ እና ዉሉን ስንፈርም ይህ መስፈረት አልተገለፀልንም፡፡ የስራ ዘርፋችን በተለያዩ ቦታዎች ከመስራት የማያግደን ከመሆኑ በላይ ተጠሪ የተሰሩ ስራዎችን ሳይረከብና ማስጠንቀቅያ ሳይሰጥ በዉል ላይ ዉል በመፈፀም ስራዉን ለሌላ ተቋራጭ መስጠቱ ተገቢ ባለመሆኑ ተጠሪ ያቀረበዉ ክስ ዉድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

በሌላም በኩል አመልካች በስር ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 06910 በተጠሪ ላይ ባቀረበው ክስ መስከረም 26 ቀን 2008ዓ/ም በተደረገዉ የህንፃ ግንባታ ዉል መሰረት የቅድመ ክፍያ ዋስትና በማስያዝ ስራ የተጀመረ እና በሶስቱም ሳይት ስራ ተሰርቶ የጥራት ችግር መኖሩ ባተረጋገጠበት ሁኔታ ተጠሪ በዉሉ ላይ ባልነበረ መስፈርት በሌላ ቦታ ላይ ስራ የለንም የሚል የሀሰት ደብዳቤ አስገብታችኋል ይቅርታ ጠይቁ በሚል ስራዉን እንዳንሰራ ካገደ በኃላ የሰራነዉ ስራ ላይ ርክክብ ሳይደረግ ተጠሪ ስራዉን ለሌላ ተቋራጭ በመስጠቱ በአጠቃላይ የብር 2,133,028.87 (ሁለት ሚሊዮን አንድ መቶ ስላሳ ሶስት ሺ ሃያ ስምንት ብር ከ87/100) ጉዳት የደረሰብን በመሆኑ ይህን ኪሳራ እንዲከፈል ይወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ተጠሪ በዚህ ክስ ላይ በሰጠው መልስ ዉሉ የተቋረጠዉ ሀሰተኛ ሰነድ በማቅረቡ በመሆኑ የተጠየቀዉ የጉዳት ካሳ የህግ መሰረት የሌለዉ ነው፤ የስራዉ መጠን በማስረጃ ያልተረጋገጠ ነው፤ አንዲሁም ለባለሙያ

እና ስራዎችን ለማከናወን የወጡ ወጭዎችን የመክፈያ ሰነድ ያልቀረበበት እና አመልካች ስራዉን እንዲያስረክቡ ተነግሯቸዉ ባለመቅረባቸዉ በገለልተኛ ባለሙያዎችና የጋራ በሆነዉ አማካሪ ድርጅት ርክክብ የተፈፀመ በመሆኑ የቀረበዉ ክስ ዉድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል።

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤት የመ/ቁ 04664 እና መ/ቁ 06910 አጣምሮ የቀረበዉን ክርክር እና መሰረጃ ከመርመረ በኃላ እንደመስፈርት ከተቀመጡት ሁኔታዎች አንዱ ተቋራጮች አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቁጠባ ቤቶች ኢንተርፕራይዝ በግንባታ ስራ ላይ አለመሳተፋቸውን ማረጋገጥ ያለባቸው ሲሆን የአሁን አመልካች ይህን ለአሰሪው ለማስረዳት ያቀረበው ማስረጃ ሀሰተኛ መሆኑ እና አመልካችም ሰነዱ የሀሰት መሆኑን በማመን አሰሪውን ይቅርታ የጠየቀ መሆኑ በቀረበው ማስረጃ ተረጋግጧል። በግንባታ ውሉ አንቀጽ 5(2) መሰረት በማታለል ተግባር የተሰማራ ተቋራጭ ዉል መሰረዝ እንደሚቻል የተስማሙ በመሆኑና ውሉም የአስተዳደር ውል በመሆኑ ተጠሪ የወሰደው የውል ማገድ እና ማቋረጥ ተግባር በአግባቡ ነው። አመልካች ተጠሪ ከአመልካች ጋር የገባዉ የግንባታ ዉል መፍረሱ እና ስራዉ መታገዱ በህግ አግባብ እና በዉላቸዉ መሰረት በመሆኑ አመልካች የጠየቀዉ የጉዳት ኪሳራ የህግ መሰረት የለዉም። የግንባታ ዉሉ በህጉ መሰረት የተቋረጠ በመሆኑ ተጨማሪ እሴት ታክስን ጨምሮ ከወሰዱት የቅድመ ክፍያ ብር 3,808,981.50(ሶስት ሚሊዮን ስምንት መቶ ስምንት ሺ ዘጠኝ መቶ ስማንያ አንድ ከ50/100) ላይ ለሶስቱም ብሎኮች ግንባታ ተጨማ አሴት ታክስን ጨምሮ ብር 1,360,463.70 (አንድ ሚሊዮን ሶስተ መቶ ስልሳ ሺ አራ መቶ ስልሳ ሶስት ከ70/100) ወጪ ማድረጋቸዉ የተረጋገጠ እና ዉሉ ከተፈፀመ ጀምሮ እስከፈረሰበት በሶስት ወር ግዜ ዉስጥ ለባለሙያና ለሰራተኛ መክፈላቸዉ የተረጋገጠ ብር 61,500.00 (ስልሳ አንድ ሺ አምስት መቶ) በድምሩ ብር 1,421,963.7 (አንድ ሚሊዮን አራት መቶ ሃያ አንድ ሺ ዘጠኝ መቶ ስልሳ ሶስት ከ70/100) ተቀንሶ የሚመጣዉን ልዩነት ብር 2,387,017.80 (ሁለት ሚሊዮን ሶስት መቶ ስማንያ ስባት ሺ አስራ ስባት ከ80/100) ስራዉ ከታገደበት እና ዉሉ ከተቋረጠበት ግዜ አንስቶ ከሚታሰብ ህጋዊ 9 % ወለድ ጋር አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል በማለት ዉሳኔ ሰጥቷል።

አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝቶ በየደረጃው ለሚገኙ የከተማው ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች ቅሬታ ቢያቀርብም የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ፀንቷል።

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው። አመልካች መስከረም 8 ቀን 2016 ዓ/ም በተፃፈ የሰበር ማመልከቻ ተፈፀመ የሚለውን ስህተት በመዘርዘር ውሳኔው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው

ተብሎ እንዲታረም ጠይቋል። የሰበር ቅሬታው ታይቶ አመልካች ሌላ የግንባታ ስራ ካለዉ አከራካሪዉን ዉል ማድረጉ ዉሉን ህገወጥ ያደርገዋል የሚል ስምምነት በሌለበት እና እንዲህ አይነት መስፈረት በህግም ሆነ በመመሪያ ባልተቀመጠበት ሁኔታ አመልካች የሰራቸዉ ስራዎች ምንም እንከን የሌለዉ ሆኖ እያለ ዉሉን ተጠሪ በዚህ ምክንያት ማቋረጡና ግንባታዉንም ለሌላ ተቋራጭ መስጠቱ አላግባብ ነዉ፤ ያቀረብኩት የካሳ ጥያቄም ዉድቅ መደረጉ ስህተት ነዉ፤ በዉሉ መሰረት የስራሁት ስራ ከ20-25% ስለመሆኑ በመዝገብ ቁጥር 04664 ላይ ተረጋግጦ እያለ ይኸዉ ከዉሉ ገንዘብ ላይ በአግባቡ ሊሰላ ሲገባዉ የስር ፍርድ ቤቶች ወደ ገንዘብ ሲቀይሩ ከብር 1,500,000.00 /አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ብር/ እንደማይበልጥ የደረሱበት ድምዳሜ በማስረጃ ተረጋገጠ የተባለዉን ፍሬ ነገር እና ህጉን የተከተለ አይደለም በሚል የቀረበዉን ቅሬታ ተጠሪ ባለበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጓል።

ተጠሪ ጥቅምት 04 ቀን 2017 ዓ/ም በሰጠው መልስ የስር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን በማስረጃ አጣርተው የሰጡት ውሳኔ ተገቢ በመሆኑ የቀረበዉ ቅሬታ ዉድቅ ሊደረግ ይገባል ብሏል። አመልካችም ክርክሩን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል።

ከፍሲል ባጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን የግራቀኙን ክርክር አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማያያዝ ቅሬታ በቀረበበት ውሳኔ የተፈፀመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል።

እንደመረመረነውም አመልካች ከተጠሪ ጋር የግንባታ ውል ስምምነት በማድረግ ቅድመ ክፍያ ብር 3,264,297.15 (ሶስት ሚሊዮን ሁለት መቶ ስልሳ አራት ሺ ሁለት መቶ ዘጠና ስባት ከ15/100) የተከፈለው መሆኑ አከራካሪ አይደለም። ተጠሪ ባቀረበው ክስ አመልካች ሀሰተኛ ማስረጃ በማቅረብ የማጭበርበር ስራ በመፈፀሙ ዉሉ በመቋረጡ በቅድመ ክፍያ የተወሰደው ገንዘብ እንዲመለሰለት ጠይቋል። አመልካች በበኩሉ ተጠሪ ለዉሉ መቋረጥ ምክንያት ብሎ የጠቀሰዉ ከዋናዉ ስራ ጋር የማይገናኝ እና ዉሉን ሲፈርም ያልተገለፀለት መሆኑን፤ በተለያዩ ቦታዎች ከመስራት የሚታገድበት ምክንያት አለመኖሩን በመጥቀስ የተጠሪ ክስ ዉድቅ እንዲሆን የተከራከረ ሲሆን በውሉ መቋረጥ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት በመሆኑም ኪሳራ እንዲከፈለው ዳኝነት ጠይቆ ተከራክሯል።

እንደሚታወቀው በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ) ላይ በግልጽ እንደተመለከተዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉን ዉሳኔዎች በማረም ላይ የተገደበ ነዉ። የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን

**ማስታወሻ፡** - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ማለት እንደሆነ ትርጓሜ ይሰጣል። በአዋጁ በትርጉም ክፍል አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለዉ አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን፣ ህግ ያላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉን ህግ የሚጠቅስ፣ ለክርክሩ አግባብነት ያለዉ ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለዉ ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፣ በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ዉድቅ በማድረግ የተወሰነ፣ በፍርድ አፈፃፀም ሂደት ከዋናዉ ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትዕዛዝ የተሰጠበት፣ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተወሰነ፣ የአስተዳደር አካል ወይም ተቋም ከህግ ዉጭ የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ በመቃረን የተወሰነ ሲሆን እና ውሳኔው ፍትህን የሚያዛባ ጉልህ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሲሆን ነው።

በተያዘው ጉዳይ የፍሬ ጉዳይ ክርክሩን ያጣራው እና ማስረጃውን የመዘነው የስር ፍርድ ቤት ለተቋራጮች ከተቀመጡት መስፈርቶች አንዱ በኢንተርፕራይዙ ሌላ ግንባታ ላይ አለመሳተፋቸውን ማረጋገጥ መሆኑን፤ አመልካች ይህን በማረጋገጥ ለአሰሪው ያቀረበው ማስረጃ ሀሰተኛ መሆኑን፤ አመልካችም ሀሰተኛ ሰነድ ማቀረቡን በማመን ይቅርታ የጠየቀበትም ማስረጃ መቅረቡን፤ ግራቀኙ ያደረጉት ውል በማታለል ተግባር መሰማራት ዉል መሰረዝ እንደሚያስከትል መደንገጉን፤ ውሉም የአስተዳደር ውል መሆኑን በማረጋገጥ የውሉ ማቋረጥ በአግባቡ ስለመሆኑ ወስኗል። ይህ የፍሬ ነገር መደምደሚያ በበላይ ፍርድ ቤቶችም ተቀባይነት አግኝቷል።

አመልካች ከተጠሪ ጋር ያደረጉት ውል የአስተዳደር ውል ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ በመሆኑ የአስተዳደር አካል የሆነው ተጠሪ ውሉን ለማፍረስ መብት ያለው ስለመሆኑ እና አመልካች ውሉ በመፍረሱ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት ቢሆን ካሳ የመጠየቅ መብት እንዳለው ከፍ/ሕ/ቁ 3180 እና 3181 ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል። ስለሆነም አመልካች ተቀባይነት የሌለው ምክንያት ተጠቅሶ የግንባታ ውሉ መቋረጡ አላግባብ ነዉ በሚል የሚያቀርበው ክርክር በስር ፍርድ ቤት በማስረጃ ተረጋገጠ የተባለውን ፍሬ ነገር እና ከፍሲል የተጠቀሰውን የህጉን ድንጋጌ ይዘት መሰረት ያደረገ ሆኖ አላገኘነውም።

አመልካች በውሉ መቋረጥ ደረሰብኝ የሚለውን ኪሳራ በተመለከተም የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን በግራቀኝ ማስረጃ አጣርቶ እንዲሁም ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ይረዳ ዘንድ ሪፖርት እንዲቀርብ በማድረግ እና ከአማካሪ ድርጅቱም አስተያየት ተቀብሎ እንዲሁም ከኮንስትራክሽን ሚ/ር የተሰጠውን ምላሽ ሁሉ መርምሮ

አመልካች የግንባታ ሥራ ለጀመረባቸው ሶስቱም ብሎኮች ግንባታ ተጨማሪ እሴት ታክስን ጨምሮ ብር 1,360,463.70 (አንድ ሚሊዮን ሶስተ መቶ ስልሳ ሺ አራ መቶ ስልሳ ሶስት ከ70/100) ወጪ ማድረጉ የተረጋገጠ መሆኑን፤ ዉሉ ከተደረገ ጀምሮ በሶስት ወር ግዜ ዉስጥ ለባለሙያና ለሰራተኛ መከፈሉ የተረጋገጠው ብር 61,500.00 (ስልሳ አንድ ሺ አምስት መቶ) መሆኑን፤ በድምሩ ብር 1,421,963.7 (አንድ ሚሊዮን አራት መቶ ሃያ አንድ ሺ ዘጠኝ መቶ ስልሳ ሶስት ከ70/100) ወጪ ስላደረገ ይህ ገንዘብ ከቅድሚያ ክፍያው ላይ ተቀንሶ የሚመጣዉን ልዩነት አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል ወስኗል። ጉዳዩ በዚህ አግባብ ተመርቶ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚሰኝ ሆኖ አላገኘነውም።

በአጠቃላይ የስር ፍርድ ቤቶች በየደረጃው ያሳለፉት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ባለመሆኑ ተከታዩን ወስነናል ።

## ው ሳ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 04664 እና መ/ቁ 06910 ሰኔ 24 ቀን 2014 ዓ/ም የሰጠዉን ዉሳኔ ፤ እንዲሁም የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 37544 ህዳር 28 ቀን 2015 ዓ/ም እና የከተማው ሰበር ችሎት በመ/ቁ 40218 ሰኔ 28 ቀን 2015 ዓ/ም በማጽናት የሰጡት ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል።
2. ዕግድ ካለ ተነስቷል።
3. የዚህ ፍርድ ቤት ክርክር ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ።

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ተመለሰ ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/0

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 253530

ጥር 27 ቀን 2017 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ብርቅነሽ እሱባለው

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች ፡- ሐረማያ ዩንቨርስቲ

ተጠሪ፡- መላ ኢንጂነሪንግ ኃ/የተ/የግል ማሕበር

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

<u>ፍርድ</u>

ጉዳዩ ከግንባታ ውል ጋር በተያያዘ በስር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ በቀረበው የዳኝነት ጥያቄ መሰረት መሆን አለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበርአቤቱታው የቀረበው የፌደራል ጠቅላይፍርድ ቤት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው በሥር ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ሲሆን ተጠሪ ተከሳሽ ነበር፡፡አመልካች በ20/01/2013 ዓ/ም ጽፎ ባቀረበው ክስ አመልካች እና ተጠሪ በነሀሴ 2009ዓ/ም እ.ኤ.አ የማስፋፊያ ግንባታ ለማከናወን ተስማምተው ተጠሪ ሳይቱን በመረከብ የግንባታ ማስፋፊያ ስራውን ጀምሮ የነበረ ቢሆንም በውሉ በተቀመጠው ጊዜ እና ጥራት የግንባታ ስራውን ማከናወን ባለመቻሉ በተደጋጋሚ ማስጠንቀቅያ ሰጥቶ ስራው 93% ላይ እያለ አመልካች ውሉን አቋርጧል፡፡ በመሆኑም ለአምስት ሕንፃዎች/ብሎኮች የስራ

ግድፈት ማስተካከያ ብር 2,031,357.91፣ ለኩሽና፣ መጽሀፍት ቤትና ምግብ ቤት ማስተካከያ ሥራ ብር 350,759.30፣ የውሉ አፈጻጸም በመዘግየቱ በውሉ አንቀጽ 49.1 መሰረት የጠቅላላ ውሉን ዋጋ 10% የደረሰ ኪሣራ ብር 5,219,807.91እና የቀሪ ሥራ ማጠናቀቂያ ብር 492,255.18በድምሩ ብር 10,107,964.5 ተጠሪ እንዲከፍል እንዲወሰንለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ተጠሪ ባቀረበው መልስ በውሉ መሰረት ለመገንባት የተስማሙትን ግንባታዎች ከአንዱ ፊኒሽንግ ስራ እና ማስተካከያ ስራ በስተቀር ሰርቼ የጨረስኩ በመሆኑና ለአገልግሎት ብቁ ስለነበሩ ውሉ ከመቋረጡ በፊት አንድ በአንድ አስረክቢያለሁ፡፡ በውሉ መሠረት አመልካች ለተጠሪ ጉድለቶችን በቅድሚያ ሳያሳውቅ የጉድለት ማስተካከያ መጠየቅ አይችልም፡፡ የኪሳራ ማቻቻያ በውሉ ልዩ ክፍል ላይ እንደተቀመጠው በአሰሪው ላይ የሚደርሰውን ኪሳራ ካለ ከውሉ አጠቃላይ 10% መብለጥ የለበትም በማለት የሚደነግግ እንጂ ስራው በጊዜ ካልተጠናቀቀ 10% የውል አጠቃላይ ክፍያ ተቋራጩ ሊከፍል ይገባል አይልም፡፡ በስራ መስሪያ ቦታ ላይ የነበሩ ጥሬ እቃዎች ግምት ብር 3,080,100፣በአመልካች የተያዘ ሪቴንሽን ብር 2,120,181.43፣ውሉእስከተቋረጠ ድረስ ለተከናወነ ግንባታ ብር 6,426,930.07 በድምሩ 9,719.048.5 የሚሆን ገንዘብ አመልካች ላይ ተጠሪ አለው፡፡ በመሆኑም ውሉ ሲቋረጥ የነበረበትን የግንባታ ደረጃ መነሻ በማድረግ በባለሙያ ቀሪ ስራ እንዲለካ እና በቦታው ላይ የነበሩት የተጠሪ ንብረቶች ተጣርቶ ውጤቱ ለፍ/ቤት እንዲቀርብ እና ተገቢው ውሳኔ እንዲሰጥ በማለት ተከራክሯል፡፡

የሐረሪ ሕዝብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ውሉ የተቋረጠው በተጠሪ ጥፋት ስለመሆኑ ከድምዳሜ ላይ ደርሶ በውላቸው አንቀጽ 49 መሰረት ለተማሪዎች መኝታ ብሎኮች ላይ ሊስተካከሉ ለሚገቡ ስራዎች ወጪ ብር 2,031,357፣ በውላቸው አንቀጽ 60 መሰረት ለቀሪው ስራ ብር 492,255፣ ለኩሽና፣ ለቤተመፅሀፍት እና ለምግብ አዳራሽ ማስተካከያ ብር 305,759፣ውሉ ለዘገየበት በርትዕ ብር 2,000,000 በድምሩ ብር 4,874,371 ተጠሪ ለአመልካች ሊከፍል ይገባል ካለ በኃላ ስራው 93% ከመድረሱ አንፃር በውላቸው አንቀጽ 48 መሠረት ለተጠሪ ከሚሰጠው እያንዳንዱ ክፍያ ላይ ተቀነሶ ከሚቀመጥ ተቀማጭ ላይ ማካካስ ይችላል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበውን ይግባኝ ባለመቀበል ሰርዟል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ አመልካችበ18/01/2016 ዓ/ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን ይዘቱም ተጠሪ የማቻቻል አቤቱታ ሳያቀርብና መልስ ሳንሰጥበት የስር ፍ/ቤት የሥነ-ሥርዓት ህጉን በመጣስ ለአመልካች በተወሰነው ብር መጠን እንዲቻቻል መወሰኑ ስህተት ነው፣የስር ፍ/ቤት ስራው በውሉ ጊዜ ሳይጠናቀቅ ለቀረበት ኪሳራ በርትዕ መወሰኑ የፌደራል መንግስት የግዢ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 16 (27)(4) ድንጋጌን እና የውላችንን አንቀጽ 49(1) ያላገናዘበ ነው፡፡የስድስት ብሎክ የተማሪዎች መኝታ ፣ኩሽና፣መፅሐፍት ቤት እና የምግብ አዳራሽ ማስተካከያ በድምሩ ብር 4,395,901.48 በማስረጃ በማስደገፍ ዳኝነት ጠይቀን እያለ ያቀረብነው ማስረጃ በምን አግባብ ውድቅ

እንደተደረገ በውሳኔው ላይ ሳይተች የገንዘብ መጠኑን በመቀነስ በግምት ብር 350,559 ተጠሪ እንዲከፈል መወሰኑ አግባብ አይደለም፤ ውሳኔው በሰበር ችሎት ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

ሰበር ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶአመልካች ከግንባታ ውል ጋር በተያያዘ ያቀረበው የዳኝነት ጥያቄ መሠረት የሥር ፍርድ ቤት አጣርቶ ለውሉ መቋረጥ ተጠሪን ሃላፊ በማድረግ ከአመልካች ብር 4,874,371 ሊከፈለው እንደሚገባ ከወሰነ በኋላ ውሉ ጸንቶ ባለበት ጊዜ ለተሠራው ስራ ክፍያ ሲፈጸም ከእያንዳንዱ ክፍያ በተጨማሪ ገንዘብ ተጠሪ በአመልካች ዘንድ ስለሚኖረው እንዲቻቻሉ በማለት ውሳኔ የሰጠው ተጠሪ የዳኝነት ክፍሎ በጠየቀው ዳኝነት መሆን አለመሆኑን ከፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 215/236-238 እና ሌሎች አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች እና የሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 86454 ከሰጠው የሕግ ትርጉም አንጻር ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ አዟል፡፡

ተጠሪ በ29/01/2017 ዓ/ም ጽፎባቀረበው መልስ በግራቀኙ መካከል የተደረገው ውል አንቀፅ 48፣49፣59፣60 እና 61 የማቻቻል ስራን እና ጥያቄን የሚያስገድድ በመሆኑአመልካች ውሉን መሠረት አድርጎ ክስ እስካቀረበ ድረስና ተጠሪም ውሉን መሠረት አድርጎ እስከተከራከረ ድረስ ፍርድ ቤቱ መዳኘት አለበት፣ ተጠሪ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕጉ መሠረት ዳኝነት ክፍሎ የማቻቻል ጥያቄ ማቅረብ ሳይጠበቅበት አመልካች ያቀረበውን ክስ ብቻ መሰረት በማድረግ ፍ/ቤቱ ውሳኔ መስጠት ይችላል፡፡ ከ98% በላይ ተጠናቆ ላለቀ ስራ እና አመልካች በአብዛኛው ተረክቦ ጥቅም ላይ ማዋሉ የተረጋገጠን ህንፃ የኪሳራ ማቻቻያ በማለት ለአመልካች የተወሰነለት ብር 2,000,000 አመልካችን የሚጠቅም እንጂ የሚጎዳ ውሳኔ አይደለም፡፡ የስራ ግድፈት ማስተካከያ ክፍያም ቢሆን አመልካች በቅድሚያ ለተጠሪ ያላሳወቀው ከመሆኑ ባለፈ የስራ ግድፈት ማስተካከያ በማለት በዳኝነት ተ.ቁ 2 ላይ የጠየቀው ብር 4,382,227.21 በክስ ዝርዝሩ ላይ ያልተመላከተ እና የተሳሳተ የድምር ውጤት በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ትክክለኛ የድምር ውጤት በሆነው ብር 2,382,117.21 ልክ የወሰነለት በመሆኑ በተወሰነለት ጉዳይ ላይ ቅሬታ ማቅረቡ ተገቢ አይደለም ብለዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የግራቀኙን ክርክር፣ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ እና ሕጉን መነሻ በማድረግ በዚህ ችሎት የተያዘውን ጭብጥ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበረው የግንባታ ውል በመቋረጡ ምክንያት ሊከፈለው የሚገባውን ክፍያ ዳኝነት የጠየቀ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ ከአመልካች ላይ ገንዘብ ያለው መሆኑን በመጥቀስ ተከራክሯል፡፡ ክርክሩን በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሰረት መምራት እና መቆጣጠር የፍርድ ቤቱ ኃላፊነት ሲሆን በተገቢው ሁኔታ ካልተመራ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ዓላማዎች የሆኑትን እንደ አንጻራዊ እውነትን የመፈለግ፣ ሥነ-ሥርዓታዊ ፍትህ፣ ክርክርን ውጤታማ፣ ወጭና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

መምራት የመሳሰሉትን ማሳካት ስለማይቻል የተከራካሪዎችን መብት ይነካል፡፡ ክርክር የሚወሰነው በተጠየቀው ዳኝነት አግባብ እንደሆነ የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 182(2) ላይ ተመልክቷል፡፡

አመልካች የሚከራከረው ተጠሪ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ሳያቀርብ ከአመልካች ላይ የሚጠይቀው ክፍያ አለ ተብሎ እንዲቻቻል መወሰኑ ሥነ-ሥርዓት ሕጉን የተከተለ አይደለም በማለት ሲሆን በዚህ ችሎት የተያዘው ጭብጥም የተጠሪ ከአመልካች የቀረኝ ክፍያ አለኝ የሚለው ክርክር ራሱን ችሎ ዳኝነት ሊጠይቅበት የሚችል መሆን አለመሆኑ እንዲመረመር በመሆኑ በጭብጡ ላይ ብቻ ተወስኖ ጉዳዩ ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 234(1)(ረ) የሚቀርብ የተከሳሽ ከሳሽነት ተከሳሽ የሆነ ወገን ከሳሽ ላይ የሚጠይቀውን ማንኛውንም ነገር እንዲወሰን የሚያቀርበውን ክስ የሚመለከት ሲሆን ክሱ ተገቢ ዳኝነት ተከፍሎበት፣ ከሳሽ የሆነው ወገን መልስ ሰጥቶበት እንደመደበኛው ክስ ክርክርና ማስረጃ ተሰምቶ ውሳኔ ሊሰጥበት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡የማቻቻል ጥያቄ ከተከሳሽ ከሳሽነት ክስ የተለየ እና በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 236 እና 237 አግባብ የመከላከያ መልስ አካል ሆኖ የሚቀርብ ነው፡፡ የማቻቻል ክርክር ተከሳሽ የሆነ ወገን ለቀረበበት ክስ ከሳሽ ከሆነው ወገን የሚፈለግ ክፍያ መኖሩንና ለክሱ ማቻቻይ ሆኖ እንዲያዝ የሚቀርብ ነው፡፡ክርክሩ የመከላከያ መልስ አካል በመሆኑ እንደተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ዳኝነት ተከፍሎበት የሚቀርብ አይደለም፡፡ ሰበር ሰሚ ችሎቱ በመዝገብ ቁጥር 177402 ላይ የማቻቻል ጥያቄ የመከላከያ መልስ አካል ሆኖ ቀርቦ ጉዳዩን መርምሮ መወሰኑን ማየት ይቻላል፡፡ ተጠሪ ለክሱ መሠረት ከሆነው ውል የሚመነጭ ከአመልካች ላይ የሚፈልገው ክፍያ መኖሩን በመጥቀስ በሥር ፍርድ ቤት ተከራክሯል፡፡ ይሕም የማቻቻል ጥያቄ ማቅረቡን የሚያሳይ ሲሆን የሥር ፍርድ ቤትም የማቻቻል ጥያቄን እንደመከላከያ ክርክር አካል በመውሰድ ጉዳዩን መመርመሩ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የፍ/ሕ/ቁ. 1831 ላይ ሁለት ሠዎች አንዱ ለአንዱ ባለዕዳ ሆኖ ሲገኝ የሁለቱን ዕዳዎች የሚያስቀር ማቻቻል እንደሚደረግ ተመልክቶ እናገኛለን፡፡ "Set-off is a mechanism of discharging one's obligation, without actually performing it, at the expense of losing one's right to ask performance of another obligation from the debtor."በማለት የተገለጸው ሥንመለከተው ማቻቻል ማለት አንድ ባለዕዳ ያለበትን ግዴታ ሳይፈጽም ነገር ግን በዚህ ሂደት ባለዕዳው ከባለመብቱ ላይ ያለውን መብት እንዲፈጸምለት የመጠየቅ መብቱን በማጣት፤ ግዴታውን የሚወጣበት ሥርዓት ነው የሚለውን እንረዳለን፡፡ በፍትሐ ብሔር ሕጉ የተመለከተው በሕግ፣ በውል ወይም በፍርድ ቤት የሚደረግ ማቻቻል በአንቀጽ 1831 የተመለከተውን የማቻቻል መሠረት የተቀረጸበትን መከተል ይገባዋል፡፡ ተጠሪም የማቻቻል ጥያቄ ያቀረበው ከአመልካች የሚጠይቀውን መብት በመተው አመልካች የሚጠይቀውን ግዴታ ለመወጣት ነው፡፡

ነገር ግን የሚቀርብ የማቻቻል ጥያቄ የፍሬ ነገር ክርክርን የሚያስከትል በመሆኑ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 246 እና ተከታዮቹ መሠረት በተነሱት የፍሬ ነገር ክርክሮች ጉዳዮች ጭብጥ መስርቶ ውሳኔ የመስጠት ኃላፊነት አለበት፡፡ ተጠሪ በመከላከያ መልሱ ላይ በስራ መስሪያ ቦታ ላይ የነበሩ ጥሬ እቃዎች ግምት ብር

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

3,080,100፣ በአመልካች የተያዘ ሪቴንሽን ብር 2,120,181.43፣ ውሉ እስከተቋረጠ ድረስ ለተከናወነ ግንባታ ብር 6,426,930.07 በድምሩ 9,719.048.50 የሚሆን ገንዘብ አመልካች ላይ እንዳለው የገለጸ ሲሆን የሥር ፍርድ ቤት እነዚህ የገንዘብ መጠኖች ተገቢ መሆን አለመሆናቸውን ሳይመረምር ፕሮጀክቱ ከደረሰበት ደረጃ አንጻር አመልካች ክስ ያቀረበበት ገንዘብን ከተጠሪ የጥራት መያዣ ገንዘብ /ሪቴንሽን/ ማካከስ ይችላል በማለት መወሰኑ በጭብጥነት ይዞ በማስረጃ በማጣራት የፍሬ ነገር መደምደሚያ ላይ ሳይደርስ በመሆኑ ውሳኔ በዚህ ረገድ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 243907 ሰኔ 27 ቀን 2015 ዓ/ም እና የሐረሪ ሕዝብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 05296 መስከረም 26 ቀን 2015 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓትመመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1)(ለ) መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2. አመልካች ብር 4,874,371.00 ሊከፈለው ይገባል የሚለው ውሳኔ ክፍል አልተነካም፤ ተጠሪ ይሕን ገንዘብ ከአመልካች የሚከፈለው የጥራት መያዣ ገንዘብ ይቻቻልለታል በማለት የተሰጠው ውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡

3. የሐረሪ ሕዝብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጠሪ ያቀረበውን የማቻቻል ጥያቄ ላይ ግራቀኙን በማከራከርና በማስረጃ በማጣራት ተጠሪ ከአመልካች ላይ ምን ያሕል ክፍያ እንዳለው በመለየት የማቻቻል ጥያቄው ላይ በሕግ መሠረት ውሳኔ እንዲሰጠበት ጉዳዩን በሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(2) መሠረት መልሠናል፡፡

4. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

- ❖ የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡ የሐረሪ ሕዝብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በውሳኔው መሠረት እንዲፈጽም አዘናል፡፡ ይጻፍ
- ❖ ውሳኔው የካቲት 05 ቀን 2017 ዓ/ም በችሎት ተነቧል፡፡
- ❖ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 253718

ጥር 26 ቀን 2017ዓ/ም

ዳኞች ፡-ገበየሁ ፈለቀ

ደረጀ አያና

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

ብርሃኑ መንግሥቱ

**አመልካች ፡- ወ/ሮ ኢየሩሳሌም ኃይሉ - ቀረቡ**

**ተጠሪዎች ፡-1. ወ/ሮ እታገኘው ኃይሉ**

**2. ወ/ሮ ዘነበች ኃይሉ**

**3. አቶ መለሰ ኃይሉ** ጠበቃ አቤል ደሳለኝ ቀረቡ

**4. ወ/ሮ ፈጠኑ ኃይሉ - ቀረቡ**

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ማጣራትን ተከትሎ የውርስ ሀብት ስለመሆኑ በተለየ ንብረት ላይ መብት ያላቸው ወራሾች ሊያገኙ ይችሉ የነበረውን ገቢ ቤቱን ከያዘው ሰው ለመጠየቅ ያላቸውን መብት የሚመለከት ነው፡፡ክርክሩ የተጀመረው በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን 1ኛ፣2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ከሳሾች፣4ኛተጠሪ ጣልቃገብ እንደዚሁም አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡በተጠሪዎች

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

የቀረበው ክስ በአጭሩ ሟቾች አቶ ሀይሉ ደነቀው እና ወ/ሮ ልንገርሽ ይሁኔ በ422 ካ.ሜ ላይ ያረፈና የቤት ቁጥር 191 የሆነ ዋና ቤትና ሰርቪስ ቤቶች የነበሯቸው ሲሆን በመ/ቁ 82464 በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት መናገሻ ምድብ ችሎት በነበረን የውርስ ሀብት ይጣራልን ክርክር ላይ የሟች አቶ ኃይሉ ደነቀው የውርስ ሀብት ተጣርቶ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡አመልካች በኑዛዜ የተላለፈላቸው 02 ክፍል ቤት ብቻ ሲሆን ክፍሎቹን እያከራዩ የሚጠቀሙበት ሆኖ በውርስ የሚደርሰንን ዋና ቤትና ሰርቪስ ቤቶችን ከህግ አግባብ ውጪ በመያዝ በዋናው ቤት እየኖሩበት አከራይተን እንዳንጠቀም በማድረግ ሰርቪስ ቤቶቹን ከተከራዩት ሰዎች ላይ የኪራዩን ገንዘብ በመሰብሰብ ለራሳቸው ጥቅም በማዋል ልናገኝ የሚገባውን ጥቅም አሳጥተውናል፡፡በመሆኑም በውሳኔው መሰረት የሚኖሩበትን ዋናውን ባለ ሶስት ክፍሉን ቤት እና የምያከራዩትን 03 ክፍል ሰርቪስ ቤቶች ከነቦታው ለቀው እንዲያስረክቡን በተደጋጋሚ ከመጠየቅ ባሻገር ጥቅምት 29 ቀን 2014 ዓ.ም ደግሞ የጹሑፍ ማስጠንቀቂያ የሰጠናቸው ቢሆንም አመልካች ቤቶቹን ለማስረከብ እንደዚሁም የቤቶቹ ኪራይ ገንዘብ ለመክፈል ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ሟች ከሞቱበት ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ ዋናው ቤት ቢከራይ በወር ብር 8000 (ስምንት ሺ.ህ) ክስ እስካቀረብንበት ጊዜ ድረሰ ያለውን የ28 ወር ብር 224,000.00 (ሁለት መቶ ሀያ አራት ሺ.ህ) እንዲከፍሉን፣የሚከራዩ 3 (ሶስት) ክፍል ሰርቪስ ቤቶች ሟች ከሞቱበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ሚያዚያ ወር ብር 1500 (አንድ ሺ. አምስት መቶ) ይከራይ የነበረው አመልካች ብር 300 (ሶስት መቶ) በመጨመር ብር 1800 (አንድ ሺ. ስምንት መቶ)፣ ሌላው 1 (አንድ) ክፍል ቤት 500 (አምስት መቶ) ይከራይ ነበረው ብር 700 (ሰባት መቶ) እና ቀሪውን 01 ክፍል ቤት በብር 1000 (አንድ ሺ.ህ) ልዩነቱ የ4 (አራት) ወር ብር 4000 (አራት ሺ.) ሟች ከሞቱበት ጊዜ ጀምሮ እስከ መጋቢት ወር መጨረሻ ክስ እስካቀረብንበት ጊዜ ድረስ ያለው ሲሰላ ሁለት ዓመት 24 (ሀያ አራት) ወር በመሆኑ ብር 70,000.00 (ሰባ ሺ.ህ) በድምሩ ብር 74,000 (ሰባ አራት ሺ.ህ) ልናገኝ የሚገባውን ጥቅም ያሳጡን ስለሆነ ዋናውን ቤት እና የሰርቪስ ቤቶቹን የኪራይ ገንዘብ ተከፍሎ እስከሚጠናቀቅበት ድረስ ከነወለዱ ታስቦ እንድከፍሉን እንዲወሰንልን የሚል ነው፡፡

አመልካችም በሰጡት መልስ በመልሳቸው የውርስ አጣሪ ሪፖርት ከቀረበ በኃላ ፍ/ቤቱ በመ/ቁ 82464 ነሐሴ 11 ቀን 2013 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ አመልካች የሚኖሩበት የወላጆቻቸው ቤት ስለሆነ የቤት ኪራይ ሊከፍሉ አይገባም ሲል ውሳኔ የሰጠበትን ጉዳይ አሁን በድጋሚ መቅረቡ አግባብነት የለውም፣ ተጠሪዎች 03 ክፍል ቤቶች ሟች ከሞቱበት ጀምሮ እስከ ሚያዚያ ወር ብር 1500 (አንድ ሺ. አምስት መቶ) ይከራይ የነበረውን ብር 300( ሶስት መቶ) በመጨመር ብር 1800 (አንድ ሺ.ህ ስምንት መቶ) ትቀበላለች ያሉት በተመለከተ ቀድሞ በነበረው ብር 1500 (አንድ ሺ.ህ አምስት መቶ) ኪራይ ነው እንጂ ብር 300 (ሶስት መቶ) አልተጨመረም፣02(ሁለት) ክፍሎች ደግሞ በፊት በወር ብር 500 (አምስት መቶ) ይከራይ የነበረው ከመስከረም ወር 2015 ዓ.ም ጀምሮ በሁለቱም ክፍሎች ብር 200

(ሁለት መቶ) ተጨምሮ በወር የሁለቱም ክፍሎች የእያንዳንዳቸው ብር 700 (ሰባት መቶ) ነው፣ከዚህ ውጭ የተጨመረ የኪራይ ገንዘብ የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

3ተኛ ተጠሪም ወደ ክርክሩ በመግባት አመልካች በኑዛዜ ባገኙት 02 ክፍል ቤት መኖር እየቻሉ የራሳቸውን እከራዩ መብቴን በመጉዳት ያልተገባ ጥቅም ስገኙ ቆይተዋል፣ሟች ወ/ሮ ልንገርሽ ይሁኔ ጥቅምት 12 ቀን 1996 ዓ.ም ባደረጉት ኑዛዜ ግማሽ ድርሻቸውን የተናዘዙልኝ ቢሆንም አመልካች ለተከራዮች በማከራየት አቤቱታ እስካቀረብኩበት ጊዜ ድረስ በኪራዩ ፍሬ እስከ አሁን ለብቻቸው እየተጠቀሙበት የሚገኙ በመሆናቸው ተጠሪዎች እስከ ነሐሴ 6 ቀን አመልካች ልትከፍለን ይገባል በማለት የጠየቁት ብር 298,000 (ሁለት መቶ ዘጠና ስምንት ሺህ የቤት ኪራይ ግማሽ ብር 149,000 (አንድ መቶ አርባ ዘጠኝ ሺህ) እና መልስ እስከሰጠሁበት የካቲት 14 ቀን ድረስ ያለውን የቤት ኪራይ ብር ብር 16,200 (አስራ ስድስት ሺህ ሁለት መቶ) በድምሩ ብር 165,200 (አንድ መቶ ስልሳ አምስት ሺህ ሁለት መቶ) እንድትከፍሉኝ እንዲወሰንልኝ ሲሉ ጠይቀዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም አመልካች በኑዛዜ ካገኙት 02 ክፍል ቤቶች ውጪ ያለውን ዋናውን ቤት እና 03 ክፍል ሰርቪስ ቤቶች ላይ የባለቤትነት መብት አለኝ በማለት ያልተከራከሩ በመሆናቸው ዋናውን ቤት እና 03 ክፍል ሰርቪስ ቤቶቹን በመልቀቅ ለተጠሪዎች እንዲያስረክቡ፣የዋናውን ቤት ኪራይ በተመለከተም በመ/ቁ 82464 ላይ የሟች አቶ ሀይሉ ደነቀውን ውርስ በማጣራት በጸደቀበት ውሳኔ ላይ ፍርድ ቤቱ የአሁን አመልካች በዋናው ቤት ላይ ኪራይ እንዲከፍሉ ሊከፍሉ በሚል የቀረበውን ጥያቄ በተመለከተ ተጠሪዎች ሟች ከሞቱ በኃላ ቤቱን እንዲለቁ ተጠይቀው ባልተቃወሙበት ኪራይ ሊከፍሉ አይገባም፡፡ ሆኖም የሟች የውርስ ሀብት ተጣርቶ ከጸደቀ በኃላ አመልካች ዋናውን ቤት ለቀው ለባለመብቶች እንዲያስረክቡ ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው ቢሆንም ለማስረከብ ፈቃደኛ ሳይሆኑ በመቅረታቸው ተጠሪዎች ቤቱን አከራይተው ሊያገኙ ይችሉ የነበረውን ገቢ ያጡ በመሆናቸው አመልካች የቤቱን ኪራይ ሊከፍሉ ይገባል፣የቀረበውንም የኪራይ መጠን ያልተቃወሙ ቢሆንም በቀረበው የአካባቢ ዋጋ መሰረት በማድረግ የሟች የውርስ ሀብት ተጣርቶ ከጸደቀበት መስከረም ወር 2013 ዓ.ም ጀምሮ ክሱ እስከቀረበበት ነሐሴ 06 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ ያለውን የ23 ወራት በድምሩ 172,000 (አንድ መቶ ሰባ ሁለት ሺህ) ከግንቦት 23 ቀን 2015 ዓ.ም ውሳኔ ከተሰጠበት ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር ታስቦ ለተጠሪዎች ሊከፍሉ ይገባል፣አመልካች የሚያከራዩአቸውን 03 ክፍል ሰርቪስ ቤቶች የኪራይ ገንዘብ ለተጠሪዎች ሊመለስ የሚገባው ስለመሆኑ ያላከራከረ ሆኖ የኪራይ መጠኑ በመሆኑ ቤቶቹ ሟች አቶ ኃሉ ደነቀ ከሞቱበት ሐምሌ 05 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ክሱ እስከቀረበበት ነሐሴ 06 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ ድረስ አመልካች ቤቱን በመያዝ በተለያየ የዋጋ መጠን ሲከራዩ የነበሩ ስለመሆናቸው ስለመሆናቸው በማስረጃ በመረጋገጡ በጠቅላላው ብር 62,500 (ስልሳ ሁለት ሺህ አምስት መቶ) ለተጠሪዎች እንዲከፍሉ በሚል ተወስኗል፡፡

አመልካች በተሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታቸውን ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም የቀረበው አቤቱታ ተቀባነት አላገኘም፡፡

አመልካች በተመሳሳይ መልኩ በተሰጠው ውሳኔ ላይ የሰበር አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡ በአመልካች ቀረበው የሰበር አቤቱታ ዘትም በአጭሩ በተጣራው የውርስ ሪፖርት መሰረት ዋናው ቤት እና 03 ክፍል ሰርቪስ ቤት የወራሾች የጋራ ሀብት ነው የተባለ ሲሆን የሀብት ክፍፍል ድርሻ ሳይፈጸም ለወራሾች አስረክባ ትውጣ በማለት የአፈፃፀም ችሎት የሰጠው ውሳኔ አግባብነት ያለው አይደለም፣ውርሱ በተጣራበት መዝገብ በዋናውን ቤት የሚኖርበት በመሆኑ ኪራይ ልትከፍል አይገባም በሚል አስቀድሞ ውሳኔ የተሰጠበት ሆኖ እያለ ከተሰጠው ውሳኔ ውጪ ኪራይ እንዲከፍል የተሰጠው ውሳኔ ተቀባይነት የለውም፣የ3(ሶስት) ክፍል ሰርቪስ ቤቶች ኪራይ በሚመለከት የውርስ አጣሪው በአጠቃላይ ብር 25,000 (ሃያ አምስት ሺ) እንዲከፍል የተሰጠውን ውሳኔ በመቀየር ጠቅላላ ብር 46,875 (አርባ ስደስት ሺ ስምንት መቶ ሰባ አምስት) የኪራይ ገንዘብ ከተጣራው የውርስ አጣሪው ፍ/ቤት ከሰጠው ውሳኔ ውጪ ከፍ በማድረግ እና በመጨመር ከነ ወለዱ ጭምር እንዲከፍል የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲታረምልኝ የሚል ነው፡፡

ይህ የሰበር ሰሚ ችሎትም የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች የውርስ ሀብት የሆነውን ዋናውና ቤት የሚኖሩበትና የማይከራየውን ተጠሪዎች አከራይተው ሊያገኙ የሚችሉትን የኪራይ ገቢ ብር 172,000 (አንድ መቶ ሰባ ሁለት ሺ) ለተጠሪዎች ድርሻቸውን እንዲከፍሉ በማለት የተሰጠው ውሳኔ አግባብነት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 82464 ነሐሴ 11 ቀን 2013 ዓ.ም የሟች አቶ ኃይሉ ደነቀውን የውርስ ሀብት በማጣራት ከሰጠው ውሳኔ ጋር በማገናዘብ ሊመረመር የሚገባው ሆኖ በመገኘቱ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት በሚል ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡

1ኛ፣2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችም በህዳር 03 ቀን 2017 ዓ.ም ባቀረቡት መልስ አመልካች ዋናውን ቤትና 3 ክፍል ሰርቪስ ቤቶች እንድታስረክበን በመጀመሪያ በቃል የጠየቅናቸው ቢሆንም ፈቃደኛ ካለመሆናቸውም በላይ ጥቅምት 29 ቀን 2014 በጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ሰጥተናቸው ማስጠንቀቂያውንም ፈርመው ተቀብለዋል፣በድጋሚም መጋቢት 09 ቀን 2014 ዓ.ም አሁንም ማስጠንቀቂያ ስንሰጣቸው ለመቀበል ፈቃደኛ ባለመሆን የውርስ ሀብት ድርሻችን ያላስረከቡን በመሆኑ የውርስ ሀብት ሪፖርት ከፀደቀበት ጊዜ ጀምሮ የውርስ ሀብቱን በድርሻችን የመረከብ ህጋዊ መብት ያለን በመሆኑ የቤቱን ኪራይ እንዲከፍሉን በሚል ያቀረብነው ዳኝነት የህግ መሠረተ ያለው ሲሆን የተሰጠው ውሳኔም መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ባለመሆኑ የቀረበው አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግ በሚል ተከራክረዋል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

4ኛ ተጠሪም ህዳር 20 ቀን 2017 ዓ.ም ባቀረቡት መልስ አመልካች በዋናው ቤት ላይ በእውነት የሚያዙበትና በህግ ጥበቃ ሊደረግለት የሚችል ምንም አይነት መብት የሌላቸው ስለሆነ የውርስ ሀብቱ ሪፖርት በመ/ቁ 82464 ነሐሴ 11 ቀን 2013 ዓ.ም ከፀደቀ በኋላ ክስ እስከቀረበበት ነሐሴ 06 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ያሳጡንን ጥቅም እንድከፍሉ የተሰጠው ውሳኔ የህግ መሰረት ያለው መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካችም ታህሳስ 4 ቀን 2017 ዓ.ም በሰጡት የመልስ መልስ ያቀረቡትን አቤቱታ በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና የግራ ቀኙ ክርክር በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን እኛም አቤቱታ ከቀረበበት የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ አግባብነት ካላቸዉ ህጎች እና ከማስቀረቢያ ነጥቡ አንፃር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡እንደመረመርነዉም ተጠሪዎች የሟች አቶ ኃይሉ ደነቀ የውርስ ሀብት እንዲጣራ ባቀረቡት አቤቱታ መሠረት የውርስ ሀብቱ ተጣርቶ የቀረበ ሲሆን ሪፖርቱም ለፍርድ ቤት ቀርቦ በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 82464 ነሐሴ 11 ቀን 2013 ዓ.ም የጸደቀ ስለመሆኑ የሚያስገነዝብ ነው፡፡ተጠሪዎችም በፍርድ ቤት ቀርቦ የጸናውን የውርስ አጣሪ ርፖርት ተከትሎ አመልካች በውርስ ሊደርሳቸው የሚገባውንና የውርስ ሀብት የሆነውን በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 06 የቤት ቁጥር 191 የሆነውን ዋና ቤት እና ሌሎች ሰርቪስ ቤቶችን በተመለከተ ለወራሾች ለማስተላለፍ ፈቃደኛ ባለመሆን በኑዛዜ የተሰጣቸውን ክፍል በማከራየት የውርስ ሀብት የሆነውን ዋናውን ቤት የሚኖሩበት ሆኖ ሌሎች ሰርቪስ ቤቶችን በማከራየት እየተጠቀሙበት የሚገኙ በመሆናቸው ሟች ከሞተበት ጊዜ ጀምሮ ያለውን የቤቶቹን ኪራ እንዲከፍሉን የሚል ነው፡፡ አመልካችም ዋናውን ቤት በተመለከተ ሟች ከመሞታቸው በፊትም ሲኖሩበት የነበረ በመሆኑ ኪራይ ሊከፍል አይገባም የሚልና ሌሎች ሰርቪስ ቤቶችን በተመለከተም አልተከራየም የሚል ሳይሆን የቀረበው የኪራይ መጠን ተገቢ አይደለም በሚል የተከራካሩ ስለመሆናቸው ከቀረበው ክርክር መረዳት የሚቻል ነው፡፡የውርስ ሀብት የሆኑትን ሌሎች ሰርቪስ ቤቶችን በተመለከተ በአመልካች ሲከራዩ የነበረ ስለመሆኑ ያላከራከረ ከመሆኑም በላይ የስር ፍርድ ቤትም ጉዳዩን በማስረጃ በማጣራት ከሟች ሞት በኃላ አመልካች ከሰርቪስ ቤቶቹ ኪራይ የተሰበሰበውን የገንዘብ መጠን በማስላት ለተጠሪዎች እንዲከፍሉ መወሰኑ በአግባቡ በመሆኑ በዚህ በኩል የቀረበው ቅሬታ ተቀባነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡በሌላም በኩል ተጠሪዎች የሚከራከሩት ዋናውን ቤት በተመለከተ አመልካች ከሟች ሞት በኃላ ሲኖሩበት የነበሩ መሆናቸውን በመጥቀስ ቤቱ ያልተከራየ ቢሆንም ለማስረከብ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው የኪራዩን መጠን በመገመት እንዲከፍሏቸው ያቀረቡ ሲሆን አመልካችም በቤቱ ውስጥ የሚኖሩ መሆናቸውንና አስቀድሞ በጸደቀው የውርስ ማጣራት መ/ቁ 82464 ላይ የኪራይ ገንዘብ መክፈል የማይገባኝ ስለመሆኑ የተወሰነ በመሆኑ የቀረበውን የዋናውን ቤት ኪራይ ሊከፍል አይገባም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

በሚል የሚከራከሩ ናቸው፡፡በመሆኑም አመልካች ዋናውን ቤት በተመለከተ ሟች ከመሞታቸው በፊትም ሲኖሩበት የነበሩ ስለመሆናቸው ያላከራከረ ሲሆን የሟች ሞትን ተከትሎ በተደረገው የውርስ ማጣራት አመልካች ዋና ቤቱን እና ሌሎች 3( ሶስት) ክፍል ሰርቪስ ቤቶች የውርስ ሀብት ስለመሆኑ በመ/ቁ 82464 ነሐሴ 11 ቀን 2013 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ የሚያሳይ ነው፡፡

ተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ የውርስ ማጣራት ሂደትን ተከትሎ በተሰጠው ውሳኔ ዋናው ቤት የተጠሪዎች የውርስ ሀብት ስለመሆኑ ተወስኖ እያለ ሊያስረክቡን ፈቃደኛ ባለመሆናቸው የውርስ ሀብቱን በማከራየት ሊናገኝ የሚገባውን ገቢ ያሳጡን በመሆኑ ከሟች ሞት በኃላ ክሱ እስከቀረበበት ቀን ድረስ ታስቦ እንዲከፈለን የሚል ሲሆን የስር ፍርድ ቤትም ከውርስ ማጣራት በፊት ነበረውንና አመልካች ሲኖሩበት የነበረውን የዋናውን ቤት ኪራይ ሊከፍሉ አይገባም በሚል የተወሰነ ሲሆን ከውርስ ማጣራት በኃላ አመልካች የውርስ ሀብቱን ለተጠሪዎች እንዲያስረክቡ በተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ የደረሳቸው ስለመሆኑ የተረጋገጠ ቢሆንም ለማስረከብ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ተጠሪዎች የውርስ ሀብቱን በማከራየት ሊያገኙ የሚችሉትን የቤት ኪራይ የመክፈል ኃላፊነት ያለባቸው በመሆኑ አመልካች የቀረበውን የዋናውን ቤት ኪራይ ብር 172,000 (አንድ መቶ ሰባ ሁለት ሺህ) ለተጠሪዎች እንዲከፍሉ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘንም፡፡

ሲጠቃለል የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች የውርስ ማጣራትን ተከትሎ ለተጠሪዎች ሊያስረክቡ የሚገባቸውንና የክርክር መነሻ ሆነውን ዋናውን ቤት ለማስረከብ ፈቃደኛ አለመሆናቸው በመረጋገጡ የውርስ ማጣራትን ተከትሎ ክስ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ ያለውንና በማስረጃ የተረጋገጠውን ብር 172,000 (አንድ መቶ ሰባ ሁለት ሺህ) የቤቱን ኪራይ ለተጠሪዎች ሊከፍሉ ይገባል በሚል የተሰጠው ውሳኔ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4) እና 10(1)(ሀ) መሰረት መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ ያላገኘን በመሆኑ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል።

## ውሳኔ

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 308469 ሐምሌ 03 ቀን 2015 ዓ.ም እንደዚሁም በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መ/ቁ 90269 ግንቦት 23 ቀን 2015 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1)(ሀ) መሠረት ጸንተዋል።

2. በዚህ መዝገብ ላይ በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መ/ቁ 94279 ጥቅምት 15 ቀን 2016 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል።

3. በዚህ ችሎት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል።

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፣ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

መ/ ዐ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 254101

ጥር 27 ቀን 2017ዓ/ም

ዳኞች፡- ገበየሁ ፈለቀ

ደረጀ አያና

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

ብርሃኑ መንግስቱ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት

ተጠሪ፡- አቶ አበራ ተፈሪ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የጉዳት ካሳን የሚመለከት ሲሆን ክሱ በጀመረበት የፌ/ከ/ፍ/ቤት አመልካች ተከሳሽ ተጠሪ ከሳሽ ነበር፡፡ ተጠሪ ያቀረቡት የክስ ይዘትም፡- የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3-53974 ኢ.ት እንዲሁም ኮድ 3-1775 ኢ.ት ለሆነው ተሽከርካሪያቸው ከአመልካች አጠቃላይ የንግድ ተሽከርካሪ የመድን ዋስትና የገዙ መሆኑን፤ ይህ መድን የተገባለት ተሽከርካሪያቸው በስራ ላይ እያለ በምዕራብ ወለጋ ዞን መንዲ ተብሎ ከሚጠራ አካባቢ ህዳር 17 ቀን 2011 ዓ.ም ያልታወቁ ግለሰቦች አስገድደው እንዲቆም አድርገው ተሽከርካሪውን፤ጭኖት የነበረውን ቢራ እና የሽያጭ ደረሰኞች ይዘው መሰወራቸውን፤ ይህ ስርቆት መፈጸሙን የተጠሪ ወኪል እንዳወቁ ወዲያውኑ ለአመልካች ድርጅት አሶሳ ቅርንጫፍ ማሳወቃቸውን፤ ከበርካታ ክትትል በኋላ ነሀሴ 16 ቀን 2011 ዓ.ም ተሳቢው ምንም ጉዳት ሳይደርስበት የተገኘ መሆኑን እና ዋናው ተሽከርካሪ ግን ተቃጥሎ መገኘቱን፤ ነሀሴ 17 ቀን 2011 ዓ.ም ፖሊስ ባደረገው ሪፖርት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ተሽከርካሪው እና ተሳቢው 2,400 ሳጥን ቢራ ጭኖ ከአ.አ ወደ አሶሳ በመጓዝ ላይ እንዳለ ህዳር 17 ቀን 2011 በሌቦች ተሰርቆ ዋናው ተሽከርካሪ በቃጠሎ ከጥቅም ውጭ ሆነ መገኘቱን መግለጹን፣አመልካች ካሳ እንዲከፍል ሲጠየቅ ደርጊቱ የተፈጸመው በሽፍቶች ነው፣ በኋላ ላይ ደግሞ ድርጊቱ የተፈጸመው በጦርነት እንቅስቃሴ እና መሰል ሁኔታዎች ነው፣ እንዲሁም ስለድርጊቱ መከሰት አላሳወቃችሁኝም በማለት የካሳ ክፍያ ጥያቄአቸውን ውድቅ ማድረጉን ገልጸው ንብረቱ በእሳት ሙሉ በሙሉ የወደመ ስለሆነ በመድን ውሉ ለንብረቱ ከተሰጠው የዋስትና ጣሪያ ብር 2,000,000.00 ከተወሰነው የአደጋ መነሻ ውስጥ ከፍተኛውን 5 % ተቀናሽ በማድረግ 1,900,000.00 ከወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፍል ይወሰንልኝ ሲሉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁን አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ ተሽከርካሪው ላይ የደረሰው አደጋ በመድን ውሉ በማይሸፈን በውንብድና በመሆኑ አመልካች ሀላፊነት የሌለበት መሆኑን፣ እንዲሁም ድርጊቱ የተፈጸመበት ሁኔታ ውንብድና እንጂ ስርቆትን የሚያሟላ አለመሆኑን፣ በተሽከርካሪው ላይ የደረሰው የእሳት ቃጠሎ የውንብድና ወንጀሉ ውጤት እንጂ በእሳት አደጋ ምክንያት የመጣ ጉዳት አለመሆኑን፣ወንበዴዎች ንብረቱን ከወሰዱ በኃላ ማቃጠላቸው ከአንድ የወንጀል ሀሳብ የመነጨ እንጂ ውንብድናው እና ቃጠሎው ከተለያዩ የወንጀል ሀሳብ የመነጨ ደርጊት አለመሆኑን፣ የመድን ሽፋን የተሰጠው ተሽከርካሪ የአገልግሎት መደቡ ጠቅላላ ጭነት ሲሆን አደጋው በደረሰበት ወቅት ግን ተሽከርካሪው በመድን ውሉ ከተጠቀሰው የአገልግሎት መደብ ውጪ በኪራይ ተላልፎ የኪራይ አገልግሎት እየሰጠ ስለነበር በመድን ውሉ መሰረት ሀላፊነት የሌለበት መሆኑን፣ሀላፊነት አለባችሁ ቢባል እንኳ ተሽከርካሪው የኪራይ አገልግሎት እንዲሰጥ ሲደረግ ከፍተኛ የአደጋ ስጋት መጨመር ስለሚኖር በአደጋ ስጋት መጨመር ምክንያት የሚኖረው የአረቦን ክፍያ ተጠሪ ከከፈሉት አረቦን ክፍያ ልዩነት ስለሚኖር ይህ በባለሙያ ከተሰላ በኋላ ካሳው ሊወሰን የሚገባ መሆኑን፣ ተጠሪ አደጋው መድረሱን ለአመልካች ወዲያውኑ ወይም እጅግ ቢዘገይ በአምስት ቀን ውስጥ ማሳወቅ ሲኖርባቸው ያሳወቁት ከአንድ አመት ከ10 ቀን በኋላ በመሆኑ አመልካች ሀላፊነት የሌለበት መሆኑን፣ ተጠሪ የተሽከርካሪውን የጉዳት መጠን እና በአደጋው ወቅት የተሽከርካሪው የገበያ ዋጋ የሚያሳይ ማስረጃ አለማቅረባቸውን፣ እንዲሁም ተጠሪ ጉዳቱ ከተሽከርካሪው ዋጋ 75% በላይ መሆኑን ስላላስረዱ አመልካች ካሳ የሚከፍልበት ምክንያት አለመኖሩን፣ ካሳ የመክፈል ሀላፊነት አለባችሁ የሚባል ከሆነም የተሽከርካሪውን ቅሪት መሸጥ መለወጥ ከሚያስችል ውክልና ጋር ለአመልካች እንዲያስረክቡ እና የእርጅና መዋጮ እንዲከፍሉ ሊወሰን የሚገባ ስለመሆኑ፣ተሽከርካሪው እንዲጠገን የሚወሰን ከሆነም የእርጅና መዋጮ ተቀናሽ ሊደረግ የሚገባ መሆኑን፣ ወለድን በተመለከተ ተጠሪ ከታህሳስ 11 ቀን 2011 ጀምሮ ክስ እስቀረበበት ጊዜ ድረስ ላለው ወለድ ዳኝነት ያልከፈሉበት በመሆኑና ወለድ እንዲከፈል የሚደረገው በአንድ የተወሰነ ቀን ለፍርድ ባለመብት ሊከፈል የሚገባ የተረጋገጠ እዳ ሲኖር በመሆኑ ወለድ ሊከፈል የሚገባው ፍርድ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ሊሆን እንደሚገባ በመግለጽ ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ በሰጠው ውሳኔ በመድን ሽፋኑ ላይ የስርቆት እና የውንብድና ተግባር የሚለው ምን አይነት ተግባር እንደሆነ ባለመገለጹ የቃላቶቹን ትርጉም ከወንጀል ህጉ አኳያ ሊታይ የሚገባ መሆኑን፣ በወቅቱ የተሽከርካሪው ሾፌር የነበረው ምስክር በህብረት የነበሩ ግለሰቦች እንደ ፖሊስ መስለው ከመኪናው ላይ ካስወረዱአቸው በኋላ በሞተር መንገዱን በመዝጋት ተሽከርካሪውን ይዘው ወደ ጫካ መግባታቸውን ማስረዳቱን፣ ይህ የምስክርነት ቃል የሚያስረዳው ተሽከርካሪው የተወሰደው የሀይል እና ማስገደድ ተግባር ከተፈጸመ በኋላ በመሆኑ ተሽከርካሪው የተወሰደው በውንብድና እንጂ በስርቆት ተግባር አለመሆኑን፣ አመልካች ለውንብድና ተግባር የሰጠው መድን ሽፋን አለመኖሩን፣ ተሽከርካሪው በውንብድና ከተወሰደ በኋላ ፖሊስ ተሽከርካሪውን ያገኘው መሆኑን፣ ተሽከርካሪው በእሳት ቃጠሎ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት መሆኑን እና የቃጠሎው ምክንያት አለመታወቁን የጊዳማ ወረዳ ፖሊስ በቀን 09/04/2012 በጻፈው ደብዳቤ ማረጋገጡን፣አመልካች ለውንብድና ተግባር የሰጠው የመድን ሽፋን ባይኖርም ተሽከርካሪው ከተወሰደበት/ከተሰረቀበት/ ሁኔታ በፖሊስ ጥረት የተገኘ እና በመድን ውሉ ላይ ሽፋን የተሰጠው የቃጠሎ ጉዳት ደርሶበት መገኘቱን፣ አመልካች ተሽከርካሪው ላይ ለሚደርስ ቃጠሎ ሽፋን የሰጠ መሆኑን፣ ቃጠሎው የደረሰው ከውንብድና ተግባሩ በኋላ በመሆኑ ብቻ አመልካች ካሳ የማይከፍልበት አግባብ አለመኖሩን ጠቅሶ አመልካች በተጠሪ ተሽከርካሪ ላይ ለደረሰው ጉዳት ካሳ የመክፈል ሀላፊነት አለበት ብሏል፡፡

አመልካች ተሽከርካሪው አደጋ በደረሰበት ወቅት የአገልግሎት መደብ ለውጥ ያደረገ በመሆኑ ሀላፊነት የለብኝም በማለት ያቀረበውን ክርክር በተመለከተ ተሽከርካሪው አደጋ የደረሰበት የአልኮል መጠጥ ጭኖ ሲጓዝ መሆኑ በግራ ቀኙ ያልተካደ መሆኑን፣ ተሽርካሪውን በኪራይ የወሰደው ተቋም ጭነት የሚያጓጓዝበት የነበረ ስለመሆኑ ለቤ/ጉ/ክ/መንግስት መግለጹን፣ በአደጋው ወቅት ተሽከርካሪው የጭነት አገልግሎት እየሰጠ የነበረ መሆኑን በመረጋገጡ ተጠሪ ተሽከርካሪውን በኪራይ መስጠታቸው አመልካችን ከሀላፊነት ነጻ አያደርገውም ሲል የአመልካችን ክርክር ውድቅ አድርጓል፡፡

አመልካች ተጠሪ አደጋ መድረሱን ወዲያውኑ ወይም በአምስት ቀናት ውስጥ ለአመልካች አላሳወቁም በማለት ያቀረበውን ክርክር በተመለከተ ደግሞ ተጠሪ ባቀረቡት ምስክሮች አደጋው መድረሱን ለአመልካች ማሳወቃቸውን ማስረዳታቸውን፣ እንዲሁም በማስረጃነት ባቀረቡት በቀን 28/03/2012 ዓ.ም ለአመልካች በጻፉት ደብዳቤ ላይ ተሽከርካሪው በቀን 17/03/2011 ተሰርቆ በ18/03/2011 ቅርንጫፍ መ/ቤት መጥቼ በወቅቱ የነበሩት ስራ አስኪያጅ ባሉበት ክሌይም ሞልቻለሁ በማለት መግለጻቸውን፣ ይህ ሰነድ የሚገኘው አመልካች ጋር ከመሆኑ አኳያ አመልካች ይህን ሰነድ አለማቅረቡ ብቻውን ፎርሙ አልተሞላም እንዲሁም የምስክሮች እና የደብዳቤው ይዘት ሀሰት ነው የሚያስብል ሆኖ አለመገኘቱን ጠቅሶ ተጠሪ በህጉ የተጣለባቸውን የማሳወቅ ግዴታ ተወጥተዋል ብሏል፡፡

በተሽርካሪው ላይ የደረሰው ውድመት በተመለከተ ደግሞ አመልካች ተሽከርካሪው አደጋ እንደደረሰበት በተጠሪ ከተገለጸለት በኋላ ተሽከርካሪውን በማንሳት የጉዳት መጠኑን መለየት ቢኖርበትም ይህን አለማድረጉን፤በተሽከርካሪው ላይ የደረሰው ጉዳት ከ75 % በታች ስለመሆኑ ያቀረበው ማስረጃ አለመኖሩን፤ ተጠሪ ተሽከርካሪው ከአገልግሎት ውጪ መሆኑን ማስረዳታቸውን፤ በዚህም ምክንያት በተጠሪ የቀረበው የጉዳቱ መጠን ሙሉ ውድመት ነው የሚለው መከራከሪያ ተቀባይነት አግኝቷል ብሏል፡፡

የካሳ መጠኑን በተመለከተ የተሽከርከሪው ዋጋ በመድን ሽፋኑ ላይ ብር 2,000,000.00 ነው ተብሎ የተገለጸ ቢሆንም ካሳ ሊከፈል የሚገባው በወቅቱ በነበረው የንብረቱ ትክክለኛ ዋጋ መሆኑን፤ የተሽከርካሪው ወቅታዊ የገበያ ዋጋም ብር 1,800.00.00 መሆኑን ማጣራቱን፤ ከዚህ ዋጋ ላይ የአደጋ መነሻ 5% ተቀናሽ ተደርጎ የሚመጣው ብር 1,750,000.00 ስለሆነ አመልካች ይህን ገንዘብ ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል ብሏል፡፡

ተጠሪ ለአመልካች የተሽከርካሪውን ቅሪት ለመሸጥ የሚያስችል ውክልና ሊሰጥ ይገባል አይገባም የሚለውን ነጥብ በተመለከተ ደግሞ አመልካች በተሽርካሪው ላይ ለደረሰ ውድመት ካሳ እንዲከፍል የተወሰነበት በመሆኑ ቅሪት አካሉን ለመውሰድ የሚችል መሆኑን፤ ነገር ግን ቅሪታ አካሉ የሚገኘው በተጠሪ እጅ ሳይሆን አደጋው በደረሰበት ቦታ በመሆኑ አመልካች ቅሪቱ የሚገኝበት ቦታ ላይ በመሄድ የመውሰድ መብት አለው ብሏል፡፡

ለተጠሪ በተወሰነው የካሳ ገንዘብ ላይ የሚታሰበውን ወለድ በተመለከተ ደግሞ ተጠሪ አደጋውን ወዲያውኑ ለአመልካች ያሳወቁ በመሆናቸው ከታህሳስ 18 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር ክፍያው ሊፈጸምላቸው ይገባል በማለት አመልካች የካሳ ክፍያ ብር 1,750,000.00 ከታህሳስ 18 ቀን 2011 ጀምሮ ከሚታሰብ 9 % ወለድ ጋር እንዲሁም የጠበቃ አበል ፤ የዳኝነት የመሳሰሉት ወጪዎችን ጨምሮ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርዟል፡፡ የአሁን ሰበር ቅሬታ የቀረበውም የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት ለማስለወጥ ነው፡፡

የሰበር ቅሬታው በአጭሩ፡- በንግድ ህግ አንቀጽ 663(1) እና የሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.76977 (ቅጽ.14) በሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ መሰረት መድን ሰጪው ሃላፊነት ያለበት በመድን ውሉ ላይ በግልጽ ተለይቶ የመድን ሽፋን ለተሰጠው አደጋ ብቻ ነው፡፡ በዚህ መሰረት አንድ መድን ሰጪ የመድን ሽፋን በሰጠው ንብረት ላይ ጉዳት ሲደርስ ካሳ እንዲከፍል የሚገደደው ለአደጋው መድረስ የቅርብ ምክንያት (Proximate Cause) በመድን ውሉ ሽፋን የተሰጠው የአደጋ ምክንያት (Risk) ከሆነ ብቻ ነው፡፡

በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በተደረገው የንግድ ተሽከርካሪ የመድን ውል ላይ ስርቆት እና የእሳት ቃጠሎ ሽፋን የተሰጣቸው የአደጋ ስጋቶች(Risks) መሆናቸው የተመለከተ ሲሆን ፣ ጉዳቱ የደረሰው በትጥቅ ወይም ያለትጥቅ በተፈጸመ ዝርፊያ፣ በሽፍትነት፣ የማገት ወይም በውንብድና ከሆነ ግን በውሉ እንደማይሸፈን በዚሁ ውል ጠቅላላ ልዩ ሁኔታዎች (Exceptions) ተራ ቁጥር 5 ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ የስር ፍርድ ቤት በተጠሪ ተሽከርካሪ ላይ ጉዳት የደረሰው በስርቆት ሳይሆን በውንብድና ድርጊት መሆኑን አረጋግጧል፡፡ ፍርድ ቤቱ አመልካች ኃላፊነት አለበት በማለት ውሳኔ የሰጠው በመድን ውሉ ክፍል ላይ የእሳት ቃጠሎ መድን ሽፋን ተሰጥቶታል በማለት ነው፡፡ በእሳት ቃጠሎ ምክንያት የሚደርስ ጉዳት ሽፋን ከተሰጣቸው የአደጋ ስጋቶች(Risks) አንዱ ቢሆንም፣ በመድን ውሉ ጠቅላላ ልዩ ሁኔታዎች (General Exceptions) ተራ ቁጥር 5 ላይ በውንብድና ድርጊት ምክንያት ተሽከርካሪው ላይ የሚደርስ ማንኛውም ጉዳት በውሉ የተገለለ (የማይሸፈን) ስለመሆኑ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ በተጠሪ ተሽከርካሪ ላይ እሳት የተነሳው በመድን ውሉ በተገለለ (በማይሸፈን) የአደጋ ምክንያት ማለትም በውንብድና ድርጊት መሆኑ እና የተጠሪን ተሽከርካሪ ያቃጠሉትም ወንበዴዎች ስለመሆናቸው በስር ፍርድ ቤቱ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ መሰረት ለተሽከርካሪው መቃጠል የቅርብ ምክንያት (Proximate Cause) የውንብድናው ድርጊት እንጂ ከውንብድናው ድርጊት የተለየ የእሳት አደጋ አይደለም፡፡ በመሆኑም የተጠሪ ተሽከርካሪ መቃጠል የቅርብ ምክንያት (Proximate Cause) በመድን ውሉ በማይሸፈን የውንብድና ድርጊት አማካኝነት መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ የስር ፍርድ ቤቱ የውንብድናውን ድርጊት እና የእሳት ቃጠሎው ሁለት የተለያዩ የአደጋ ምክንያቶች በማስመሰል አመልካች ኃላፊነት አለበት በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የመድን ሕግ መርሕ የሆነውን “Principle of Proximate Cause” (የቅርብ ምክንያት መርሕ) የሚጥስ በመሆኑ ሊሻር የሚገባው ነው፡፡

ፍርድ ቤቱ ተሽከርካሪውን በአደጋው ቦታ እንደሚገኝ በክርክር ወቅት ስለተገለጸ ብቻ አመልካች አደጋው ቦታ ድረስ ሂዶ መውሰድ ይችላል በማለት የሰጠው ውሳኔ የህግ መሰረት የሌለው ነው፡፡ ምክንያቱም በመድን ውሉ ጠቅላላ ሁኔታዎች ተ.ቁ.2 ሶስተኛው አረፍተ ነገር መሰረት የመድን ሽፋን የተሰጠው ተሽከርካሪ አደጋ ሲደርስበት ያለጠባቂ መተው እንደሌለበት እና ተጨማሪ ጉዳት እንዳይደርስበት መጠበቅ እንዳለበት የተመለከተ ሲሆን፣ በፍ/ብ/ህ/ቁ.1802 እና የሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.54021 በሰጠው ውሳኔ መሰረትም አንድ ካሳ የሚጠይቅ ወገን ሊደርስ የሚችለውን ኪሳራ የመቀነስ ሕጋዊ ግዴታ አለበት፡፡ ተጠሪ በወንበዴዎች ጉዳት የደረሰበት ተሽከርካሪ ተጨማሪ ጉዳት እንዳይደርስበት ማስጠበቅ እና ከአደጋው ቦታ አስነስቶ ማስቀመጥ ሲገባው ከአራት አመት በላይ በአደጋው ቦታ አለማንሳቱ በክርክሩ ወቅት በተረጋገጠበት እና በአሁኑ ሰዓት ቅሪቱ መኖሩ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ የስር ፍርድ ቤት ቅሪቱን ከአደጋው ቦታ ሂዳችሁ ውሰዱ ሲል የሰጠው ውሳኔ ተገቢነት የሌለው ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አንድ ሰው አንድን ነገር ለሌላ ሰው አስረከበ የሚባለው

የተጠቀሰውን ነገር ለሚመለከተው ሰው በእጁ ሲያስረክብ ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች የተሽከርካሪውን ቅሪት አደጋው ቦታ ድረስ ሂዶ መውሰድ ይችላል ተብሎ መወሰኑ የውሉን እና ህጉን መሰረት ያላደረገ ከመሆኑም በላይ ተሽከርካሪው ልዩ ተንቀሳቃሽ በመሆኑ አመልካች አደጋው ቦታ ሂዶ ቅሪቱን ለመውሰድ እና ስመ ሀብቱን ለማዛወር የባለቤትነት ማስረጃ እና የውክልና ሰነድ አስፈላጊ በመሆኑ ተጠሪ የተሽከርካሪውን ቅሪት ከዋና ሊብሬ እና ቅሪቱን መሸጥ መለወጥ ከሚያስችል ውክልና፣ ክሊራንስ እና ሌሎች አስፈላጊ ሰነዶች ጋር ለአመልካች ሊያስረክበው ይገባል ተብሎ የስር ፍርድ ቤቱ ውሳኔ እንዲሻር እንጠይቃለን፡፡

የስር ፍርድ ቤቱ ከታህሳስ 17 ቀን 2011ዓ/ም ጀምሮ ክፍያው እስከሚፈጸም ድረስ ታስቦ ለተጠሪ ህጋዊ ወለድ እንዲከፈለው ወስኗል፡፡ ይሁን እንጂ የሰበር ሰሚ ችሎት በኮ/መ/ቁ.133203 በሰጠው ውሳኔ ካሳው እንደማይስተናገድ እያወቀ ክሱን ሳይከፍት ለዘገየበት ጊዜ ወለድ ሊከፈል እንደማይገባ እና ወለድ ሊታሰብ የሚገባው ክሱ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ስለመሆኑ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ወለዱን ክሱ ከቀረበበት ህዳር 9 ቀን 2013 ዓ/ም ጀምሮ ታስቦ እንዲከፈለው መወሰን ሲገባው ከታህሳስ 18 ቀን 2011ዓ/ም ጀምሮ እንዲታሰብ መወሰኑ የሰበር ሰሚ ችሎቱ የሰጠውን ውሳኔ የሚጻረር ስለሆነ አላግባብ የተወሰነው የሁለት አመት ወለድ እንዲቀነስልን የሚሉ ናቸው፡፡

ተጠሪ ለሰበር ቅሬታው በሰጡት መልስ አመልካች የውንብድና ተግባሩን የመጨረሻ እና ገዢ በሆነ የፍርድ ውሳኔ አድርጎ ማቅረቡ ተገቢ አለመሆኑን፤ የስር ፍ/ቤት የውንብድና ተግባር ነው የሚል መደምደሚያ ላይ የደረሰው በራሱ አረዳድ እንጂ በሚመለከተው የወንጀል ፍ/ቤት ክስ ቀርቦ ፍርድ በመሰጠቱ አለመሆኑን፤ የስር ፍ/ቤት ተሽርካሪው የተወሰደበትን ሂደት በተመለከተ የውንብድና ተግባር ነው ሲል የደረሰበት መደምደሚያ ገዢ እና የመጨረሻ ሆኖ ሊወሰድ የሚችልበት አግባብ አለመኖሩን፤ ተጠሪም የሚቃወሙ መሆኑን፤አመልካች በተጠሪ ተሽከርካሪ ላይ ጉዳት የደረሰው በመድን ውሉ ላይ ሽፋን ባልተሰጠው የውንብድና ድርጊት መሆኑ የተረጋገጠ ነው ሲል ያቀረበው ቅሬታ ባልተረጋገጠ ፍሬ ነገር ላይ የተመሰረተ ስለመሆኑ፤ ተሽከርካሪው የተወሰደበት ሁኔታ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 670 እና 671 ስር የተመለከቱትን የውንብድና ተግባር የሚያቋቁሙ ግዙፍ ሁኔታዎች ተሟልተው ያልተፈጸሙ መሆኑን እና በተደረገው የፖሊስ ምርመራም የተረጋገጠው እና በሪፖርቶቹ ላይ የተመለከተው ተሽከርካሪው ተሰርቆ የተወሰደ ስለመሆኑ፤ ተሽከርካሪው የተወሰደበት ተግባር በውንብድና ወይስ በስርቆት የሚለው ሊተረጎም የሚገባው በውል ህጉ ስለ ውል አተረጓጎም የተቀመጡ ድንጋጌዎችን ተፈጻሚ በማድረግ ሊሆን እንደሚገባ፤ የመድን ውሉ በአመልካች የተዘጋጀ በመሆኑ ለአመልካች በሚጠቅም መልኩ ተለጥጦ ሊተረጎም የማይገባ መሆኑን፤አመልካች Proximate Cause /የቅርብ ምክንያት/ መርህን መሰረት በማድረግ በተሽከርካሪው ላይ ለደረሰው ጉዳት ቅርብ የሆነው ምክንያት የውንብድና ደርጊቱ ነው ሲል ያቀረበው ቅሬታ ከመድን ስራ ይዘት እና አፈጻጸም መርህ፤

አላማ እና መንፈስ ውጭ ስለመሆኑ፣ እንዲሁም ተሸከርካሪው መሰረቁ የተገለጸው ህዳር 17 ቀን 2011 ሆኖ አብሮ ተሰርቆ የነበረው ተሳቢ ምንም ጉዳት ሳይደርስበት ተጠሪ በነሀሴ 16 ቀን 2011 የተረከቡ መሆኑ እና ዋናው ተሸከርካሪ የተገኘው ከጊዜ በኋላ ተቃጥሎ መገኘቱ ክርክር ያልቀረበበት እና በማስረጃ የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች ሆነው ሳለ አመልካች እነዚህ ሁለቱ ድርጊቶች የተለያዩ ሆነው መታየት የለባቸውም ሲል የሚያቀርበው ክርክር የጠቀሰውን መርህ ብቻ ሳይሆን የፍሬ ነገርም ድጋፍ የሌለው መሆኑን ጠቅሰው አመልካች ሀላፊነት የለብኝም ሲል ያቀረበው ቅሬታ ውደቅ እንዲደረግ ጠይቀዋል፡፡

በሌላ በኩል ተሸከርካሪው ባልታወቁ ሰዎች ተሰርቆ ወደ ማይታወቅ ስፍራ መወሰዱ እና በፖሊስ ክትትል መገኘቱ እየታወቀ፣ እንዲሁም አካባቢው በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ምክንያት የግለሰቦች እንቅስቃሴ የተገደበበት መሆኑ እየታወቀ ተጠሪ ንብረቱን ማስጠበቅ አልቻለም፣ሙሉ በሙሉ ንብረቱ በእሳት ወድሞ የተገኘውን ንብረትም ተጨማሪ ኪሳራ እንዳይደርስበት መከላከል ነበረበት የሚለው የአመልካች ቅሬታ ተገቢነት የለውም ብለዋል፡፡

በመጨረሻም ወለድን በተመለከተ አመልካች የመድን ሽፋን የሰጠው ተሸከርካሪ አደጋ ከደረሰበት በኋላ በመድን ውሉ የተቀመጡ የካሳ መክፈያ አማራጮች ተጠቅሞ ተገቢውን ካሳ ያልከፈለ በመሆኑ ካሳው ቢከፈል ኖሮ ገንዘቡ ሊያስገኝ የሚችለውን ህጋዊ ወለድ አመልካች እንዲከፍል መወሰኑ ተገቢ መሆኑን እና ቅሬታው የህግ ድጋፍም የለውም ብለዋል፡፡

አመልካች የመልስ መልስ ያቀረበ ሲሆን ክርክሩን አጠናክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለፀውን ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ፣ ከጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እና ቅሬታው ለሰበር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ነጥብ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተው መርምሮታል፡፡

ከንግድ ህጉ አንቀፅ 654(1) ግልፅ ድንጋጌ መረዳት እንደሚቻለው የኢንሹራንስ ውል ፖሊሲ ሲባል የኢንሹራንስ ሰጭው የኢንሹራንስ መግቢያ ዋጋ (ፕሪሚየም) ተቀብሎ በውሉ የተመለከተው አደጋ በደረሰ ጊዜ ኢንሹራንስ ለገባው ሰው የተወሰነ ገንዘብ ለመክፈል ግዴታ የሚገባበት ውል ነው፡፡ ኢንሹራንስ ሰጪው ለሚደርሰው ጉዳት ሁሉ ተጠያቂ ሊሆን አይችልም፡፡ተጠያቂ ሊሆን የሚችለው የመድን ሽፋን ለገባበት ጉዳይ ነው፡፡የንግድ ህጉ ቁጥር 663(1) ኢንሹራንስ ሰጪው በውሉ ለተመለከተው አደጋ ኢንሹራንስ ለገባው ሰው መድን ሊሆን የሚችለው እና የሚገደደው በውሉ የተመለከተው አደጋ በደረሰ ጊዜ ብቻ መሆኑን ከንግድ ህጉ አንቀፅ 654(1) የምንረዳው ነው፡፡መድን ሰጪው በመድን ውሉ የተመላከተው አደጋ የደረሰ እንደሆነ መድን ገቢውን አደጋ በደረሰበት ወይም በውሉ በተመላከተው ጊዜ ውስጥ የመካስ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ በን/ሕ/ቁጥር 663(1) እና 665

መመልከቱም ይህንኑ የሚያጠናክር ነው፡፡መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘብነዉ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የመድን ሽፋን ዉል መኖሩ እና የመድን ሽፋን የተሰጠዉ ተሽከርካሪ በእሳት አደጋ ጉዳት የደረሰበት መሆኑ ያላከራከረ ሲሆን የደረሰው ጉዳት በመድን ውሉ የተገለፀው እና የመድን ሽፋን የተሰጠው ጉዳት ነው ወይስ አይደለም ተገቢው ምላሽ ሊሰጠው የሚገባው የዚህ መዝገብ አንኳር ጭብጥ መሆኑን ግራ ቀኙ ከስር ፍርድ ቤት ጀምሮ ካደረጓቸው ክርክሮች የምንረዳው ነው፡፡

በመሰረቱ የደረሰውን ጉዳት ኢንሹራንስ ሰጪው የመሸፈን የውል ግዴታ አለበት ወይስ የለበትም የሚለው ጭብጥ አከራካሪ የሚሆነው የተለያዩ ምክንያቶች ከአደጋው መድረስ ጋር ተያይዘው ለአደጋው መድረስ ዋናው ምክንያት የትኛው ነው የሚለው መሰረታዊ የክርክሩ ጭብጥ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡

ኢንሹራንስ ሰጪው የደረሰውን ጉዳት የመካስ ሃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም የሚለውን ጭብጥ ለመወሰን የቅርብ ምክንያት (Proximate cause) ን በመስፈሪያነት መጠቀም በተለያዩ ሀገራት የተለመደ ሲሆን ይህ መስፈርትም “In jure non remota causa, sed proxima spectator.”( In law, not the remote butthe proximate cause is considered.)ከኢንሹራንስ የመድን ሰጪው ሀላፊነት አንፃር የሩቅ ሳይሆን የቅርብ ምክንያት ከግምት ውስጥ የሚገባ መሆኑን የሚያመለክተው የሕግ መርህ መሰረት ያደረገ መሆኑን በዘርፉ ከተደረጉት የተለያዩት ጥናቶች የምንገነዘበው ነው፡፡መድን ሰጪው የደረሰውን ጉዳት የመካስ ሀላፊነት አለበት ወይስ የለበትም የሚለውን ለመወሰን ለጉዳቱ መሰረታዊው ምክንያት (Root cause of the Loss) ምንድነው;መሰረታዊው ምክንያት የተገለለ መሆን አለመሆኑ(If it is excluded from the policy or not) እና መሰረታዊው ምክንያት የቅርብ ምክንያት መሆኑ ሲረጋገጥ(Whether or not there was a proximate cause) ሲሆን የቅርብ ምክንያት ከጊዜ ይልቅ ከውጤት ጋር የሚያያዝ መሆኑ፣ አንድ ምክንያት ለደረሰው ጉዳት የቅርብ ምክንያት ነው ሊባል የሚችለው ለደረሰው ጉዳት አውራ(Dominant)፣ቀጥተኛ (Direct) ና ውጤታማ (Effective) ምክንያት ሆኖ ሲገኝ መሆኑን በዘርፉ የተደረጉ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይ በእሳት ቃጠሎ ምክንያት የሚደርስ ጉዳት ሽፋን ከተሰጣቸው የአደጋ ስጋቶች(Risks) አንዱ መሆኑ፣ እንዲሁም በውንብድና ድርጊት ምክንያት ተሽከርካሪው ላይ የሚደርስ ማንኛውም ጉዳት በመድን ውሉ ጠቅላላ ልዩ ሁኔታዎች (General Exceptions) ተራ ቁጥር 5 መሰረት የተገለለ (የማይሸፈን) መሆኑ በግራ ቀኙ ክርክር ያልቀረበበት ሲሆን የመድን ሽፋን የተሰጠው መኪና ከነተሳቢው ከተጠሪ እጅ በቅድሚያ የወጣው በስርቆት ሳይሆን በውንብድና ድርጊት መሆኑ ማስረጃን የመስማት፣የመመርመርና የመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ነጥብ ነው፡፡በተጠሪ ተሽከርካሪ ላይ እሳት የተነሳው በመድን ውሉ በተገለለ (በማይሸፈን) የአደጋ ምክንያት ማለትም በውንብድና ድርጊት መሆኑ በሌላ አነጋገር የተጠሪን ተሽከርካሪ ያቃጠሉት ወንበዴዎች ስለመሆናቸው በስር ፍርድ ቤቶች አለመረጋገጡ፣በኑሮ የልማድ ህግ መሰረት በወንበዴዎች የተወሰደ

መኪና በተለመደ ሁኔታ የሚቃጠል መሆኑ አለመረጋገጡ የወንበዴዎቹ ድርጊትና የእሳት አዳጋው ሁለት የተለያዩ ምክንያቶች መሆናቸውን ያሳያል፡፡

አከራካሪው መኪና ህዳር 17 ቀን 2011 ዓም በሀይልና በማስገደድ ከነተሳቢውና ከነጭነቱ የተወሰደ ሆኖ ዋናው መኪና ብቻ ተቃጥሎ የተገኘው ነሀሴ 16 ቀን 2011 ዓም መሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች መረጋገጡ የእሳት አደጋው በመኪናው ላይ ለደረሰው ጉዳት አውራ(Dominant)፣ቀጥተኛ (Direct) ና ውጤታማ (Effective) የሆነ የቅርብ ምክንያት (Proximate cause) መሆኑን ያሳያል፡፡ይህ ከሆነ ደግሞ የስር ፍርድ ቤቶች የእሳት ቃጠሎው የመድን ሽፋን የተሰጠው አደጋ መሆኑን በመጥቀስ አመልካች በተጠሪ ተሽከርካሪ ላይ ለደረሰው ጉዳት ካሳ የመክፈል ሀላፊነት አለበት በማለት መደምደማቸው የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሌላውን የማስቀረቢያ ነጥብ በተመለከተ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ለተጠሪ የካሳ ክፍያ ብር 1,750,000.00 ከታህሳስ 18 ቀን 2011 ጀምሮ ከሚታሰብ 9 % ወለድ ጋር ሊከፍሉ ይገባል በማለት ውሳኔውን ያሳረፈው ታህሳስ 18 ቀን 2011 ዓም ተጠሪ ለአመልካች አደጋውን ያሳወቁበት ጊዜ መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት መሆኑን የስር ፍርድ ቤት መዝገብ ያሳያል፡፡የስር ፍርድ ቤት ለወለዱ ስሌት ታህሳስ 18 ቀን 2011 ዓም ን መነሻ ያደረገው ስለ አደጋው ተጠሪ ለአመልካች ያሳወቀበት ቀን መሆኑን መነሻ በማድረግ ቢሆንም በእለቱ የተሰጠ የክፍያ ማስጠንቀቂያ አለመኖሩ፣መኪናው ተቃጥሎ የተገኘውም ከዚህ ጊዜ በኋላ ነሀሴ 16 ቀን 2011 ዓም መሆኑ፣ክሱም እጅግ ዘግይቶ ህዳር 09 ቀን 2013 ዓም በተጠሪ የቀረበ መሆኑ የስር ፍርድ ቤት ታህሳስ 18 ቀን 2011 ዓም ን ለወለዱ አቆጣጠር መነሻ ያደረገው አግባብ ባልሆነ መልኩ መሆኑን ስለሚያሳይ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ውሳኔ

1.የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.252223 ጥር 25 ቀን 2015 ዓም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔና ይህንን ውሳኔ በማፅናት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በይ/መ/ቁ.244776 ሀምሌ 19 ቀን 2015 ዓም የሰጠው ውሳኔ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስነስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9(1)(ለ) መሰረት ተሻሽሏል፡፡

1.1. አመልካች በተጠሪ ተሽከርካሪ ላይ ለደረሰው ጉዳት ካሳ የመክፈል ሀላፊነት ያለበት መሆኑን በማመልከት አመልካች ለተጠሪ የካሳ ክፍያ ብር 1,750,000.00 (አንድ ሚሊዮን ሰባት መቶ ሀምሳ ሺህ ብር) ሊከፍል ይገባል በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

1.2. አመልካች ለተጠሪ የካሳ ክፍያ ብር 1,750,000.00 (አንድ ሚሊዮን ሰባት መቶ ሀምሳ ሺህ ብር) ሊከፍል የሚገባው ክሱ ከቀረበበት ህዳር 09 ቀን 2013 ዓም ጀምሮ ገንዘቡ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር ነው ብለናል፡፡

2.ግራ ቀኙ በሰበር ክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪ እና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

ጉዳዩ ውሳኔ ስላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

**የሰ/መ/ቁ 254696**

**ጥር 27 ቀን 2017ዓ/ም**

ዳኞች፡-ገበየሁ ፈለቀ

ደረጀ አያና

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

ብርሃኑ መንግሥቱ

አመልካች፡- ወ/ሮ ሳፊያ ከድር - ቀርቧል

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. ሐጂ አማን ሐጂ ሁሴን

2ኛ. አቶ ሙክታር ሐጂ አማን

3ኛ. ወ/ሮ ገኖ ኢብራሂም

4ኛ. ወ/ሮ ቀመሪያ ሁሴን

5ኛ. ወ/ሮ ገኖ ሁሴን

6ኛ. አቶ መሀመድአሚን ሐጂ አማን

(1ኛ–5ኛ) ጠበቃ አህመድ አብዳ ቀርቧል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ጉዳዩ የውርስ ድርሻን የሚመለከት ሲሆን ክሱ በቀረበበት ኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሰት ባሌ ዞን በርበሬ ወረዳ ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ 1ኛ ተጠሪ ተከሳሽ፤ ከ2ኛ እስከ 6ኛ ያሉ ተጠሪዎች ደግሞ

ጣልቃ ገብ ተከራካሪዎች ነበሩ፡፡ አመልካች ያቀረቡት ክስ ይዘት፡- የ1ኛ ተጠሪ ሚስት የነበሩት እናታቸው ወ/ሮ ነኢማ ሀሚድ በሞት ከዚህ ዓለም መለየታቸውንና የሟች ወራሾች 7(ሰባት) እንደሆኑ ፤ ሟች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር አፍርተዋል የሚሉትን መገኛቸው እና አዋሳኞቹ በክሱ ላይ ከተመለከቱት ከተራ ቁጥር 1-10 ከተዘረዘሩ ንብረቶች የሟች 50% የሚስት ድርሻ መሆኑን በመግለጽ 1ኛ ተጠሪ የውርስ ድርሻቸውን እንዲያክፈሏቸው እንዲወሰንላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

1ኛ ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መልስ ከአመልካች እናት ጋር የነበራቸው ጋብቻ በ1997 ዓ.ም በበርበሬ ወረዳ ፍርድ ቤት ፈርሶ በጋራ ያፈሩትንና ንብረቶችንም ህዳር 30 ቀን 1997 ዓ.ም በተደረገ ስምምነት መከፋፈላቸውን፤ አመልካች የሟች እና የ1ኛ ተጠሪ የጋራ ንብረቶች ናቸው በማለት ዘርዝረው ካቀረቡት ንብረትና ይዞታ ውስጥ በ6ኛ ተራ ቁጥር ላይ የተመለከተው የ2ኛ ተጠሪ ሲሆን በ9ኛ ተራ ቁጥር ላይ የተመለከተው የ6ኛ ተጠሪ መሆኑን፤ ቀሪዎቹ ንብረቶች ከሟች የአመልካች እናት ጋር ከተለያዩ በኋላ ከ3ኛ-5ኛ ካሉት ተጠሪዎች ጋር እንዳፈሩ በመግለጽ ክሱ ውደቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

2ኛ ተጠሪ በጣልቃ ገብነት አቤቱታቸው በክሱ በተራ ቁጥር 6 የተመለከተው ንብረት የግላቸው መሆኑን ፤6ኛ ተጠሪ በክሱ ተራ ቁጥር 9 የተጠቀሰው ንብረት የእሳቸው መሆኑን፤እንዲሁም ከ3ኛ እስከ 5ኛ ያሉ ተጠሪዎች ደግሞ አመልካች በክሱ በተራ ቁጥር 6ኛ እና 9ኛ ከጠቀሱት ውጭ ያሉት ቀሪ ንብረቶች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ያፈሩት የጋራ ንብረቶች መሆናቸውን፤የአመልካች እናት በ1997 ዓ.ም ንብረት ተካፍላ ስለወጣች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ያፈራባቸው ንብረቶች፤2ኛ እና6ኛ ተጠሪዎች ደግሞ የግላቸው የሆኑት ንብረቶች ከክርክሩ ውስጥ እንዲወጡላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካች በክሱ ላይ የተመለከቱት ሁሉም ንብረቶች ሟች እናታቸው ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ያፈሩት የባልና ሚስት ንብረቶች ስለሆኑ የሥር ጣልቃ ገቦች አቤቱታ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት የተከራካሩ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ በበኩላቸው የሥር ጣልቃ ገቦች ባቀረቡት አቤቱታ መሠረት ውሳኔ ብሰጥ ተቃውሞ የለኝም በማለት ለጣልቃ ገብነት አቤቱታው ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣን የተመለከተው የበርበሬ ወረዳ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ሰምቶ በሰጠው ውሳኔ በሟች እና 1ኛ ተጠሪ ስም የተከፈተ መዝገብ አለመኖሩ ከፕሮቶኮል መዝገብ እና ዳታ ቤዝ ተፈልጎ ባለመገኘቱ በሟች እና 1ኛ ተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ መፍረሱን ተከትሎ የንብረት ክፍፍል ማድረጋቸውን የሚገልጽ ውሳኔ በፍርድ ቤቱ ባይገኝም በአመልካችና 1ኛ ተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ በዚያው ፍርድ ቤት በተሰጠ የፍቺ ውሳኔ መፍረሱን፤ፍርድ ቤቱ የንብረት ክፍፍሉን በተመለከተ ለሽምግልና መርቶ ሟች እና 2ኛ ተጠሪ የነበራቸውን ንብረቶች ህዳር 30 ቀን 1997 ዓ.ም በተደረገ ስምምነት ተከፋፍለው ክፍፍሉን የሚያመለክተው ሰነድም ለፍርድ ቤት ቀርቦ መዝገቡ መዘጋቱ በግራ ቀኙ ምስክሮች፤እንዲሁም ህዳር 30 ቀን 1997 ዓ.ም በሟች እና 1ኛ ተጠሪ መካከል ስምምነት መደረጉን የሚያመለክት ሰነድ ቀርቦ መረጋገጡን፤በክሱ በተራ ቁጥር 6 እና

9 ሥር የተጠቀሱት ንብረቶች የ2ኛ እና 6ኛ ተጠሪዎች መሆኑን፤ቀሪዎቹ ንብረቶች 1ኛ ተጠሪ ከአመልካች እናት ጋር ከተፋቱ በኋላ ከ3ኛ እስከ 5ኛ ድረስ ካሉት ተጠሪዎች ጋር የተፈሩ መሆኑ በሰው እና ሰነድ ማስረጃ ተረጋግጧል በሚል አመልካች ያቀረቡትን ክስ ውድቅ አድርጓል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ይግባኝ ለባሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ይግባኙ ያስቀርባል በማለት ግራ ቀኙን አከራክሮ በሰጠው ውሳኔ በሟች የአመልካች እናት እና 2ኛ ተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍርድ ቤት ውሳኔ መፍረሱን የሚያመለክት ማስረጃ ባይቀርብም ሟቿ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር የነበራቸው ትዳር በፍርድ ቤት በተሰጠ የፍቺ ውሳኔ መፍረሱንና የአመልካች እናት በህይወት እያለች ንብረት ተካፍላ የሄደች መሆኑ ከንብረት ክፍፍል መዝገብ ቁጥር 101/93 እንዲሁም በግራ ቀኙ የሰው ምስክሮች ተረጋግጧል በማለት የበርበሬ ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔን አጽንቷል፡፡ ይግባኝ ሰሚው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ደቡብ ምድብ ቋሚ ችሎትም በክልሉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 69/1995 አንቀጽ 98 ድንጋጌ መሠረት የፍቺ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን የፍርድ ቤት በመሆኑ የፍቺ ውሳኔ ተሰጥቷል የሚል ተከራካሪ ወገን ሊያቀርብ የሚገባው ቀዳሚ ማስረጃ በፍርድ ቤት የተሰጠ የፍቺ ውሳኔ ግልባጭ ቢሆንም የፍቺ ውሳኔ የተሰጠበት መዝገብ አለመኖሩ በበርበሬ ወረዳ ፍርድ ቤት ስለተገለፀ ሟች እና 1ኛ ተጠሪ በትዳር ውስጥ እያሉ በጋራ ያፈሩትን ንብረት የተከፋፈሉ መሆኑን ህዳር 30 ቀን 1997 ዓ.ም ከተደረገው ስምምነት እና በመዝገብ ቁጥር 101/93 ላይ የተሰጠው የውሳኔ ግልባጭ ማመልከቱን ጠቅሶ፤አመልካች የሟች እናቴ ግማሽ በለድርሻ የሆኑበት የውርስ ድርሻዬ ይሰጠኝ በማለት ዘርዝሮ ያቀረቡት ንብረቶች ሟች የአመልካች እናት ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ያፈሩት ሳይሆን 1ኛ ተጠሪ ሚስቶቹ ከሆኑት ከ3ኛ-5ኛ ካሉት ተጠሪዎች ጋር ያፈሩ መሆኑ በግራ ቀኙ ምስክሮች ተረጋግጧል፡፡ በክሱ በተራ ቁጥር 6 እና 9 ላይ የተመለከቱት ንብረቶችም የ2ኛ እና 6ኛ ተጠሪዎች መሆኑን የተጠሪዎቹ ምስክሮች ከአመልካች ምስክሮች በተሸለ መልኩ ስላረጋገጡ አመልካች ከሟች እናታቸው በውርስ ሊያገኙ የምችሉት ንብረት አለመኖሩ ተረጋግጦ የተሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም በማለት አመልካች ለሁለተኛ ጊዜ ያቀረቡት የይግባኝ አቤቱታ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 377 መሠረት ሰርዟል፡፡ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር አጣሪ ችሎትም በየደረጃው ያሉት ጉዳዩን የተመለከቱት የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም በማለት አመልካች ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ በኦሮሚያ ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 216/1 መሠረት ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ሊቀርብ አይገባም በማለት ሰርዟል፡፡

የሰበር ቅሬታ የቀረበው በየደረጃው ጉዳዩን የተመለከቱት የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት በሰበር ለማሳረም ሆኖ የሰበር አቤቱታው ይዘት በአጭሩ፡- 1ኛ ተጠሪ ከአመልካች እናት ጋር ባልና ሚስት መሆናቸውን አምነው ጋብቻቸው ከአመልካች እናት ሞት በፊት በፍርድ ቤት በተሰጠ የፍቺ ውሳኔ ፈርሷል በማለት ያቀረቡት ክርክር

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

አግባብነት ባለው ማስረጃ ሳይጣራ በሀሰት ተቀነባብሮ የቀረበ የሰው ምስክር መሠረት አድርጎ ውሳኔ መሰጠቱ ስህተት ነው፡፡ በሚች የአመልካች እናት እና 1ኛ ተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ መፍረሱ በሰው ምስክር ሊረጋገጥ የሚችል አይደለም፡፡ 1ኛ ተጠሪ ከአመልካች እናት ጋር ያላቸውን ንብረትና ይዞታ ህዳር 30 ቀን 1997 ዓ.ም በተደረገ ስምምነት ተከፋፍለናል ቢሉም ለበርበሬ ወረዳ ፍርድ ቤት ቀርቦ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 277/1 መሠረት ተመዝግቦ ከመዝገብ ጋር የተያዘ ስምምነት መኖሩ ተጣርቶ እንዲቀርብ ታዞ በአመልካች እናት ስም እና በ1ኛ ተጠሪ ስም የተከፈተ መዝገብ አለመኖሩ ከዳታ ቤዝ እና ከባለጉዳይ ፕሮቶኮል መዝገብ ተጣርቶ የቀረበው መግለጫ አላግባብ ታልፎ የተሰጠው ውሳኔ ስህተት ሆኖእያለ ጉዳዩ በይግባኝ የተመለከቱት የሥር ፍርድ ቤቶች የበርበሬ ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔን ማጽናታቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው፡፡ በአመልካች እናት ስም እና በ1ኛ ተጠሪ ስም የተከፈተ መዝገብ አለመኖሩ ተረጋግጦ እያለ እና ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች የጠቀሱት የመዝገብ ቁጥር 101/93 1ኛ ተጠሪ ከሚች የአመልካች እናት ጋር የንብረት ክፍፍል አድርገናል ከሚሉት 1997 ዓ.ም በፊት በ1993 ዓ.ም የተከፈተ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው ማስረጃ ለውሳኔ መሠረት መሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው፡፡ በክሱ 6ኛ እና 9ኛ ተራ ቁጥር ላይ የተጠቀሱት ንብረቶች የስር 1ኛ እና 3ኛ ጣልቃ ገቦች የአሁን 2ኛ እና 6ኛ ተጠሪዎች ለመሆኑ ከሚመለከተው አካል የጽሁፍ ማስረጃ ሳይቀርብ መወሰኑ ስህተት ነው፡፡ 2ኛ እና 6ኛ ተጠሪዎች በክሱ ተራ ቁጥር 6ኛ እና 9ኛ ላይ የሚገኙት ንብረቶች ይዞታዎች እንደቅደምተከተላቸው የግላችን ነው ከማለት ውጪ ይዞታው የእነሱ መሆኑንና በስማቸው መመዝገቡን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከሚመለከተው የመንግስት ተቋም ሳይቀርብ የሰው ምስክር ብቻ መሰረት አድርጎ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ በየደረጃው ጉዳዩን የተመለከቱት ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ተሽሮ 1ኛ ተጠሪ አመልካች ከሚች እናታቸው የሚደርሳቸውን የውርስ ንብረት እንዲያካፍሏቸው እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡

በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 6/1 መሠረት ለሰበር ሰሚው ችሎቱ የተመራው የሰበር አቤቱታ በሰበር ሰሚ ችሎቱ ተመርምሮ የአመልካች አውራሽ ከመሞታቸው በፊት ባለቤታቸው ከሑኑት 1ኛ ተጠሪ ጋር የነበራቸው ጋብቻ በፍርድ ቤት የፍቺ ውሳኔ የፈረሰ መሆን አለመሆኑን እና በሽማግሌዎች ተፈጽሟል የተባለው የንብረት ክፍፍል ሰነድ ፍርድ ቤት ቀርቦ መመዝገቡ መዝገቡ ቀርቦ ሳይጣራ የንብረት ክፍፍል ተደርጎ የአመልካች እናት ድርሻቸውን ወስደዋል ተብሎ የመወሰኑ አግባብነት ሊጣራ ይገባል ተብሎ ተጠሪዎች ተከታዩን መልስ ሰጥተዋል፡፡

ተጠሪዎች ነሃሴ 17 ቀን 2016 ዓ.ም በጋራ በመሆን አመልካች ላቀረቡት የሰበር ቅሬታ በሰጡት መልስ፡- በአመልካች እናት እና በ1ኛ ተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ ፈርሶ በሽማግሌዎች ህዳር 30 ቀን 1997 ዓ.ም የተደረገው የንብረት ክፍፍል ስምምነት በፅሁፍ ቀርቦ ከመዝገብ ቁጥር 101/93 ጋር ተያይዞ እያለ አመልካች ሚች እናቷ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ያፈራችውን ንብረት እንዳልተካፈለች ያቀረበች አቤቱታ ከእውነት የራቀ ነው፡፡ በአመልካች እናት እና በ1ኛ ተጠሪ መካከል በሽማግሌዎች የተደረገው

የንብረት ክፍፍል ቀርቦ በመዝገብ ቁጥር 101/1993 ተመዝግቦ እያለ አመልካች አልተመዘገበም በማለት ያቀረቡት አቤቱታ የህግ መሰረት ስለሌለው ውድቅ እንዲደረግልን፡፡ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ከተራ ቁጥር 1-10 ዘርዝረው ካቀረቡት ንብረት እና የይዞታ በ6ኛ እና 9ኛ ተራ ቁጥር ላይ ከተመለከቱት ውጪ ያሉት የአመልካች እናት ሳይሆን 1ኛ ተጠሪ ከ3ኛ፤4ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች ጋር ያፈሩት የጋራ ንብረት እና ይዞታ ሲሆን ቀሪው 6ኛ እና 9ኛ ተራ ቁጥር ላይ የተጠቀሰው ንብረት እና ይዞታ የ2ኛ እና የ6ኛ ተጠሪዎች የግላቸው ንብረት እና ይዞታ መሆኑን የበርበሬ ወረዳ ፍርድ ቤት አግባብነት ባለው ማስረጃ አረጋግጦ የአመልካች ጥያቄ ተገቢነት የሌለው መሆኑን አጣርቶ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የበርበሬ ወረዳ ፍርድ ቤት በአመልካች እናት እና 1ኛ ተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ መፍረሱን፤በጋራ ያፈሩትን ንብረት መካፈላቸውን አጣርቶ ውሳኔ ስለሰጠ ሟች የአመልካች እናት በአከራካሪዎቹ ንብረቶች ላይ ድርሻ የሌላቸው በመሆኑ ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ውድቅ ይሁንልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለ መልኩ የተመለከተው የግራ ቀኝ ክርክር እና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ውሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንፃር የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ንብረት ማፋራት መሠረታዊ መብት መሆኑና ማንኛውም ሰው በጉልበቱ፤በመፍጠር ችሎታው ወይም በካፒታሉ ያፈራው ንብረት ባለቤት እንደሆነ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አዋጅ ቁጥር 1/1987 አንቀጽ 40/1 እና(2) ጣምራ ንባብ መረዳት ይቻላል፡፡ ሰቶች ንብረት የማፍራት፤ የማስተዳደር፤የመቆጣጠር፤ የመጠቀምና የማስተላለፍ መብት ያላቸው መሆኑን አንቀጽ 35/2 ያስረዳናል፡፡ ባለሀብነት ከሁሉ የሰፋ መብት መሆኑንና በሕግ ካልተገደበ በቀር ባለሀብቱ ሀብቱን በፈለገው መንገድ ልገለገልበት የሚችል መሆኑን ከፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 1204 እና 1205 ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ባለሀብትነት በሕግ ወይንም ባለጉዳዮች በሚያደርጓቸው ሕጋዊያን ተግባሮች ሊተላለፍ መቻሉን፤ሀብትነቱ ለሌላ ሰው ስተላለፍ የቀደመው ሀብትነት ቀሪ እንደሚሆን ከፍትሐብሔር ሕጉ ቁጥር 1184፤1185 እና 1189 ድንጋጌ መረዳት ይቻላል። ውርስ አንዱ የንብረት መብት መተላለፊያ መንገድ ነው፡፡ ወራሾች በፍትሐ ብሔር ህጉ ቁጥር 826/2 መሠረት ሊወርሱ የሚችሉት ሟች በሕይወት እያለ የነበረውን መብት ሆኖ የሟች ልጆች የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾ መሆናቸውንና ከውርሱም ትክክል ድርሻ የሚያገኙ መሆኑን የፍትሐ ብሔር ህጉ ቁጥር 842 ንዑስ ቁጥር1 እና2 ሥር ተመልክቷል፡፡

ንብረት በግል ወይም በጋራ ሊፈራ ይችላል፡፡ የባልና ሚስት የጋራ የንብረት ባለሀብትነት የሚፈጠረው በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 1258 ላይ እንደተመለከተው በጋራ ባለሀብቶች መካከል በሚደረግ

ስምምነት ሳይሆን በሕግ ነው፡፡ Matrimonial property is created principally by operation of law, and not by will of parties unlike joint ownership property. Therefore, matrimonial property, unlike co-owership is statutory creation, applying exclusively to married couples as one of the effects of their matrimomial union. ይህ ማለት ግን ተጋቢዎች አስቀድሞ ወደ ትዳር ውስጥ ከመግባታቸው በፊት በግል የነበራቸውን ንብረት በጋብቻ ውል የጋራ ማድረግን አይከለክልም፡፡ ሌላው የባልና ሚስት ንብረት ከጋራ ባለሀብትነት የሚለየው ጋብቻ ፀንቶ እያለ ማንኛውም ተገቢ የንብረት ክፍፍል ጥያቄ ማቅረብ አይችልም፡፡ የጋራ ባለሀብቶች ቁጥር ከሁለት በላይ ሊሆን የሚችል ሲሆን በባልና ሚስት የጋራ ባለሀብትነት ግን በመርህ ደረጃ ቁጥሩ ከሁለት አይበልጥም፡፡

ጋብቻ ሕጋዊ ድርጊት (juridical act) በመሆኑ ሕጋዊ ውጤትን ያስከትላል፡፡ ጋብቻ የተፈፀመበት ሥርዓት ከግምት ሳይገባ ተመሳሳይ ወጤት አለው፡፡ ከጋብቻ ውጤቶች መካከል በውል ሊቀየሩ ወይም ሊሻሻሉ የሚችሉ ያሉ ቢሆንም በውል ሊቀየሩ ወይም ሊሻሻሉ የማይችሉ አስገዳጅ ውጤቶች አሉ፡፡ ጋብቻ በግላዊ ግንኙነት ላይ ከሚኖረው ውጤቶች ጥቂቶቹ በጋብቻ አፈፃፀም፣ባልና ሚስት በጋብቻ ዘመንና በፊቺ ጊዜ እኩል መብት ያላቸው መሆኑን፣መከባበርና መተጋገዝ ያለባቸው መሆኑን፣እንዲሁም ጋብቻ ከንብረት አንፃር የሚያስከትለው ውጤት ተጠቃሾች መሆናቸው የኦሮሚያ ክልል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 69/1995 አንቀጽ 65፣አንቀጽ 73 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ሥር ተመልክቷል፡፡

የኦሮሚያ ክልል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 69/1995 አንቀጽ 19 እና ተከተዮቹ ድንጋጌዎች መሠረት ሶስት የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓቶች ያሉ ሲሆን እነሱም በክብር መዝገብ ሹም ፊት የሚደረግ ጋብቻ፣በሃይማኖት እና በባህል ሥርዓት መሠረት የሚፈፀሙ ጋብቻዎች ናቸው። ህጉ በማንኛውም የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓት የሚፈጸመው ጋብቻ ማሟላት የሚገባውን ቅድመ ሁኔታዎችን ከአንቀጽ 25 እና ቀጥሎ ባሉት አንቀጾች ሥር የሚዘረዝር ሲሆን፣ በማንኛውም የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓት የተፈፀመ ጋብቻ ልዩነት የማይደረግበት መሆኑንና ተመሳሳይ ሕጋዊ ውጤት እንደሚኖረው አንቀጽ 56 እና 96 ይደነግጋሉ። በሕግ የፀና ጋብቻ መኖሩ የሚረጋገጠው በጋብቻ የምስክር ወረቀት ሆኖ የጋብቻ የምስክር ወረቀት ለማቅረብ በማይቻልበት ጊዜ ጋብቻ ለመፈፀሙ አሳማኝ እና በቂ ማስረጃ በማቅረብ ማስረዳት እንደሚቻል ከሕጉ አንቀጽ 92 እና 93 ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል። ጋብቻ በተጋቢዎቹ ግላዊ ግንኙነት እና ንብረት ላይ የሚኖረው ውጤት በሕጉ የተመለከተ ሲሆን የንብረት ግንኙነትን አስመልክቶ ከአንቀጽ 73 ጋብቻ በሚፈፀሚበት ጊዜ እና በጋብቻ ውስጥ እያሉ በግል በውርስ ወይንም በስጦታ የተገኙ ንብረቶች የግል ሲሆኑ፣በጋብቻ ውስጥ በተጋቢዎቹ የግል ጥረት ወይንም ከግል ንብረት የሚገኝ ገቢ (ፍሬው) የጋራ ሃብቶች እንደሆኑ ያመለክታል። አንቀጽ 78 መሠረት በጋብቻ ውስጥ የተፈራ፣በጋብቻ ውስጥ በግብይት የተገኘ ሆኖ የግል መሆኑ በፍርድ ቤት ያልፀደቀ ንብረት

እንዲሁም በስጦታ ወይንም በኑዛዜ ለተጋቢዎቹ የተላለፈ የጋራ ንብረት እንደሆነ ተደግጓል። በጋብቻ ውስጥ የተፈራ ንብረት አንዱ ተጋቢ የግሉ መሆኑን ካላስረዳ በቀር የጋራ እንደሆነ ሕጉ ግምት እንደምወስድ አንቀጽ 79 ይስገነዝበናል። የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍልን አስመልክቶ ጋብቻ ሲፈፀም ወይንም በፍቺ ወቅት የተደረገ የሚፀና ሕጋዊ ውል በማይኖርበት ጊዜ የባልና ሚስት ንብረት ተጣርቶ የግል የሆነውን ባለንብረቱ የሚወስድ ሲሆን፤የጋራ የሆነውን ንብረት በሕጉ አግባብ ባልና ሚስቱ እንዲካፈሉ የሚወሰን መሆኑን የኦሮሚያ ክልል የቤተሰብ ሕግ ቁጥር 69/1995 አንቀጽ 112 እና ተከታዮቹ ያመለክታሉ፡፡ በተጋቢዎቹ እጅ ያሉ ንብረቶች በማን ስም ተመዘገቡ የሚለው ከግምት ውስጥ ሳይገባ የጋራ ሀብት እንደሆኑ ስለሚቆጠር የግል ንብረቴ ነው የሚል ተጋቢ የግሉ/ሏ መሆኑን የማስረዳት ግዴታን እንደለበት/እንዳለባት አንቀጽ 79(1) እና 113(1) ያመለክታሉ፡፡

ሰበር ሰሚ ችሎቶች በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 80 መሠረት በመጨረሻ ውሳኔ ላይ በተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት እንጂ ማስረጃው ተመዝኖ የተደረሠበትን የፍሬ ነገር ድምዳሜን መርምሮ የመቀየር ሥልጣን ባይኖራቸውም ማስረጃ ለመመዘን ሥልጣን የተሠጠው ፍርድ ቤት ማስረጃ ሲቀበል የተከራካሪዎችን እኩል የመደመጥ መብት ካላከበረ፤ የማስረዳት ሸክም (burden of production) የማን ነው የሚለውን ካልለየ፤የማስረጃ ተቀባይነትና ተገቢነት ላይ መከተል የሚገባውን ሥርዓት ካልተከተለ፤ በምዘና ጊዜ የሁሉንም ተከራካሪዎች ማስረጃ አብሮ ካልመዘነ፤የተለየ የማስረዳት ደረጃ (standard of proof) የሚጠይቁ ጉዳዮችን በሚጠይቀው ደረጃ ልክ መረጋገጡን ካላሳየ እና በመሠረታዊ ሕግ ሆነ በሥነ-ሥርዓት ሕግ ያሉትን የማስረጃ ሕጎችና መርሆች ካላከበረ ጉዳዩ የማስረጃ ምዘና ሳይሆን የሕግ አተረጓጎም ስህተት ይሆናል፡፡ የማስረጃ ህግ ስህተት ተፈጽመዋል ተብሎ ጉዳዩ ለሰበር ቀርቦ የሚታረመው የማስረጃው ተቀባይነት፤የማስረጃ አቀባበል ሥርዓት፤የማስረጃ ምርመራና ምዘና የሚከናወንበትን ሂደት የሚደነግጉ አስገዳጅ የማስረጃ ሕግ ድንጋጌዎች ስህተትና በዚህ ምክንያት የመብት ጥሰት እና የፍትህ መጓደል ሲኖር በሰበር ሊታረም ይችላል፡፡ (የሰበር መዝገብ ቁጥር 29261 እና 22297 ይመለከቷል)

ፍርድ ቤት እና ሌሎች የዳኝነት ሥልጣን የተሰጣቸው አካላት ባልታመነ (በተካደ) ፍሬ ነገር ላይ በግራ ቀኙ የተቆጠሩትን ትክክለኛ ፍትሕ ለመስጠት አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎችን በመስማት፤ የማስረጃውን ተዓማንነት በመመርመር እና በመመዘን የተከራካሪዎቹን እኩልነት እና ፍትሕ የማግኘት መብት የማክበር ግዴታ አለባቸው፡፡ በግራቀኙ ተከራካሪ ወገኖች የተቆጠረ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ማስረጃ በአግባቡ መስማት ዋነኛ የክርክር አመራር ሥርዓት መሰረታዊ መርህ ነው፡፡ ይህ ማለት ግን በተከራካሪ ወገኖች የተቆጠሩት ሁሉም ማስረጃዎች የግድ መሰማት አለባቸው ማለት አይደለም፡፡ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 138 ድንጋጌ መሰረት ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው ወይንም ከነገሩ ጋር ግኙነት የሌለውን ማስረጃ ተቀባይነት ያላገኘበትን ግልጽ ምክንያት ጠቅሶ ማለፍ

ይቻላል፡፡ የቀረበን ክርክር አግባብነት ባለው የተቆጠረ ወይንም ሌላ ማስረጃ ሳያጣሩ ውሳኔ መስጠት የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉን ቀጥር 111,249,255,257,259 እና ሌሎች ድንጋጌዎችን የሚፃረር ተገቢውን የክርክር አመራር ሥርዓት ያልተከተለ በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት የሰበር ሰሚ ችሎቱ በሰበር መዝገብ ቁጥር 38683,95026 እና በሌሎች በርካታ መዘግብት ላይ አስገዳጅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም ፍርድ ቤቶች ከውሳኔ ሊደርሱ የሚገባው የተከራካሪ ወገኖችን የመሰማት፤የመከላከል ብሎም በእኩልነት መርህ የመዳኘት መብትን በጠበቀ መልኩ መሆን እንዳለበት፤ክርክር ሊወሰን የሚገባው በቀረበው ማስረጃ እና በሕጉ መሠረት መሆኑን፤በግልጽ የቀረበን ክርክር በተቆጠረ ማስረጃ ወይንም አግባብነት ባለው መንገድ እንዲጣራ(እንድነጥር) ሳይደግ የሚሰጥ ውሳኔ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን የሰበር ሰሚው ችሎት አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ (የሰበር መዝገብ ቁጥር 36848 , 39853 እና 52546 ይመለከቷል፡፡)

በተያዘው ጉዳይ አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ጋብቻ የነበራቸው እናታቸው ትዳር በሞት መፍረሱን ተከትሎ ሟች እናታቸው ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በትዳር እያሉ ካፈሩት ንብረት የውርስ ድርሻቸውን እንዲያክፍሏቸ እንዲወስንላቸው ላቀረቡት ክስ 1ኛ ተጠሪ ጋር ትዳር የነበራቸው መሆኑን በማመንና አመልካች የሟች ወራሽ መሆናቸውን ሳይቃወሙ ከሟች ጋር የነበራቸው ጋብቻ የፈረሰው በሞት ሳይሆን በ1997 ዓ.ም በበርበሬ ወረዳ ፍርድ ቤት በተላለፈ የፍቺ ውሳኔ መሆኑንና የፍቺ ውሳኔውን ተከትሎ በጋራ ያፈሯቸውን ንብረቶችንም ህዳር 30 ቀን 1997 ዓ.ም በተደረገ ስምምነት መከፋፈላቸውን በመግለጽ ለአመልካች የሚያካፍሉት የሟች የውርስ ሀብት በእጃቸው እንደሌለ ተከራካረዋል፡፡ 1ኛ ተጠሪ ከሟች የአመልካች እናት ጋር ትዳር የነበራቸው መሆኑንና በትዳር ውስጥ እያሉ ንብረት ያፈሩ መሆኑን አምነው ትዳራቸው በፍርድ ቤት ውሳኔ ፈርሶ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ክፍፍል አድርገናል በማለት የሚከራካሩ ከመሆኑ አንፃር ይህንን ክርክራቸው አግባብነት ያለው ማስረጃ በማቅረብ ማስረዳት አለማስረዳታቸው መመርመር ያለበት ጭብጥ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ማስረጃ አከራካሪ የሆነው ጭብጥ እውነተኛነት የሚረጋገጥበት ወይም ውድቅ የሚሆንበት ዘዴ ነው፡፡ የአከራካሪውን ፍሬ ነገር መኖር ወይም አለመኖር የማስረዳት ሸክም ያለበት ተከራካሪ ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው ተገቢ ማስረጃዎችን አቅርቦ የማስረዳት ግዴታውን መወጣት እንዳለበት የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 258-260 እና በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 2001 ያመለክታል፡፡ ስለሆነም ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ ያለበት ወገን በማስረጃው የማሳመን ግዴታ (Burden of Presuasion) ይኖርባታል፡፡ በኦሮሚያ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 69/1995 አንቀጽ 97 ድንጋጌ መሰረት ፍቺ ጋብቻ ከሚፈርስባቸው ምክንያቶች ውስጥ አንዱ መሆኑ፤ፍቺ እና የፍቺ ውጤት የሆነውን የባልና ሚስት ንብረት አጣርቶ በአንቀጽ 112 እና ተከታዮች መሰረት ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን የፍርድ ቤት ብቸኛ ሥልጣን መሆኑን ከአንቀጽ 98 እና አንቀጽ 99 ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ይህ ማለት ግን ባልና ሚስቱ በፍቺ እና የፍቺ ውጤት ላይ ስምምነት ማድረግ አይችሉም ማለት አይደለም፡፡ የፍቺ ውጤት የፍቺ ውሳኔን እንደሚከተል የአንቀጽ 110(2) እና (6) ድንጋጌዎች የሚያመለክቱ በመሆኑ ፍቺ ሳይኖር(ጋብቻ ፀንቶ እንያለ) በፍቺ ውጤት ላይ አስቀድሞ ስምምነት ሊደረግ የሚችልበት የሕግ አግባብ አይኖርም፡፡ ጋብቻ በፍቺ ከፈረሰ በኋላ በፍቺ ውጤት ላይ ባልና ሚስቱ ስምምነት ማድረግ የሚችሉ ቢሆንም የፍቺ ውጤት በስምምነት በሚያልቅበት ወቅት፤በሽማግሌዎች ወይም በባለሞያዎች በሚወሰንበት ጊዜ ውሳኔው ተፈፃሚነት የሚኖረው ለፍርድ ቤት ቀርቦ የባልና ሚስቱ ትክክለኛ ፍላጎት መሆኑና ፍላጎታቸውን በነፃ የሰጡ መሆኑ፤ስምምነቱ ሕግ እና ሞራልን የማይቃረን አለመሆኑ ተረጋግጦ ተቀባይነት አግኝቶ ስጸድቅ ብቻ እንደሆነ የኦሮሚያ ክልል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 69/1995 አንቀጽ 103(1)፤(2) እና 111/5 ድንጋጌ ያስገነዝበናል፡፡

እጃችን ላይ ባለው ጉዳይ አከራካሪው ፍሬ ነገር የሟች እና 1ኛ ተጠሪ ጋብቻ በፍርድ ቤት ውሳኔ መፍረስ አለመፍረሱንና የፍቺ ውጤት የሆነው የንብረት ክፍፍል መደረግ አለመድረጉ ሲሆን ይህ ፍሬ ነገር የሚረጋገጠው ዋናውን የፍርድ ቤት ውሳኔ ወይንም ትክክለኛነቱ የተረጋገጠውን ግልባጭ በማቅረብ ቢሆንም የበርበሬ ወረዳ ፍርድ ቤት በሟች የአመልካች እናት እና በ1ኛ ተጠሪ ስም የተከፈተ መዝገብ ከፕሮቶኮል መዝገብ እና ዳታ ቤዝ ተፈልጎ አለመገኙቱን አጣርቷል፡፡ ህዳር 30 ቀን 1997 ዓ.ም በሟች እና 1ኛ ተጠሪ መካከል ስምምነት መደረጉን ያመለክታል የተባለው የሰነድ ማስረጃም በቤተሰብ ሕጉ በተመለከተው አግባብ ለፍርድ ቀርቦ ተቀባይነት ያገኘ ማስረጃ ባልሆነበት የበርበሬ ወረዳ ፍርድ ቤት የሰው ምስክሮች መሠረት አድርጎ በባልና ሚስቱ መካከል አስቀድሞ የንብረት ክፍፍል መደረጉ ተረጋግጧል በማለት የአመልካችን የሟች ውርስ ይገባኛል ክስ ውድቅ ማድረጉ፤ የበርበሬ ወረዳ ፍርድ ቤት በሟች እና 1ኛ ተጠሪ ስም የተከፈተ መዝገብ አለመኖሩን አረጋግጦ እያለ ይግባኝ ሰሚው የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሟች የአመልካች እናት እና 1ኛ ተጠሪ መካከል የነበረው ትዳር መፍረሱን የሚያመለክት አንዳች ማስረጃ ባልቀረበበት ጋብቻ ፀንቶ እያለ የንብረት ክፍፍል ሊቀድም እንደማይችል እየታወቀ በባልና ሚስቱ መካከል የፍቺ ውጤት የሆነው የንብረት ክፍፍል በመዝገብ ቁጥር 101/93 ተፈጽሟል ማለቱ፤ጉዳዩን አመልካች ለሁለተኛ ጊዜ ባቀረቡት የይግባኝ አቤቱታ የተመለከተው ይግባኝ ሰሚው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ደቡብ ምድብ ቋሚ ችሎትም የፍቺ ውጤት የሆነውን የንብረት ድርሻ ክፍፍል ክስ ለማቅረብ ፍቺ መቅደም ያለበት መሆኑንና ፍቺ መኖሩን ለማስረዳት ቀዳሚው ማስረጃ በፍርድ ቤት የተሰጠ የፍቺ ውሳኔ ግልባጭ መሆኑን ብቀበልም በተጠሪ በኩል የፍቺ ውሳኔ መቼ እና በየትኛው የመዝገብ ቁጥር እንደተሰጠ ግልጽ ክርክር ባልቀረበበት፤በሟች እና 1ኛ ተጠሪ ስም የተከፈተ መዝገብ የለም የሚለውን የበርበሬ ወረዳ ፍርድ ቤት መግለጫን የፍቺ ውሳኔ የተሰጠበት መዝገብ እንዳልተገኘ(እንደጠፋ) መስዶ ክርክሩን በሰው ምስክር ማስረዳት ይቻላል በሚል በልምድ በዳበረው አሰራር የንብረት ዝርዝር የምቀርበውና የባልና ሚስት የሆነው ንብረት ተጣርቶ ውሳኔ የሚያገኝው የፍቺ ውሳኔ በተሰጠበት

መዝገብ ላይ ሆኖእያ በሚች እና 1ኛ ተጠሪ ስም የተከፈተ መዝገብ አለመኖሩ ተረጋግጦ ባለበት ሚች እና 1ኛ ተጠሪ በትዳር ውስጥ እያሉ በጋራ ያፈሩትን ንብረት የተከፋፈሉ መሆኑን ህዳር 30 ቀን 1997 ዓ.ም ከተደረገው ስምምነት እና በመዝገብ ቁጥር 101/93 ላይ የተሰጠው የውሳኔ ግልባጭ ማመልከቱን ጠቅሶ የሥር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ማጽናቱ፤የሰበር አጣሪ ችሎቱ የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መሰረዙ ከላይ የተጠቀሱትን የክልሉን የቤተሰብ ሕግ አስገዳጅ ድንጋጌዎችን፤እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት አስገዳጅ ውሳኔዎችን የሚቃረን መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ቀጣዩ ተወስኗል፡፡

## ውሳኔ

1. የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር አጣሪው ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 436831 ጥቅምት 27 ቀን 2016 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ፤ይግባኝ ሰሚው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ደቡብ ምድብ ቋሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 408840 ጥቅምት 1 ቀን 2016 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ፤የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 35647 ግንቦት 25 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ እና ትዕዛዝ ፤እንዲሁም የበርበሬ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 20869 ጥር 24 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ፍርድ እና ትዕዛዝ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ- ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 9(1/ለ) መሠረት **ተሽሯል፡፡**

2. የበርበሬ ወረዳ ፍርድ ቤት በውሳኔ የዘጋውን መዝገብ ቁጥር 20869 በማንቀሳቀስ በፍርድ ሀተታው ውስጥ በተመለከተው አግባብ ሚች የአመልካች እናት በህይወት እያሉ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር የነበራቸው ትዳር በፍርድ ቤት በተሰጠ የፍቺ ውሳኔ ፈርሶ የንብረት ክፍፍል ማድረግ አለማድረጋቸውን ለጉዳዩ አግባብነት ባለው ማስረጃ አጣርቶ ተገቢ የሆነውን ህጋዊ ውሳኔ እንዲሰጥ መዝገቡ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 9/2 መሠረት መልሰንለታል፡፡

3. ነሃሴ 3 ቀን 2016 ዓ.ም በመዝገቡ ላይ የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡

4. የዕግድ ትዕዛዝ መነሳቱ ለበርበሬ ወረዳ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ይድረስ፡፡

5. የውሳኔው ትክክለኛ ግልባጭ ለበርበሬ ወረዳ ፍርድ ቤት ይድረስ፡፡

6. በዚህ ችሎት የተደረገው ክርክር ላስከተለው ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ውሳኔ አግኝቶ ስለተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 254862

ጥር 27 ቀን 2017ዓ.ም

**ዳኞች ፡- ገበየሁ ፈለቀ**

**ደረጀ አያና**

**ደጀኔ አያንሳ**

**ኑረዲን ከድር**

**ብርሃኑ መንግስቱ**

**አመልካች ፡- ወ/ሮ በላይነሽ ጫላ - ጠበቃ ብርሃኑ በቀለ ቀረቡ**

**ተጠሪ ፡- አቶ ሸዋንግዛው ሽብሩ**

*መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡*

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በጋብቻ ዉስጥ ተፈርቷል የተባለ ሀብት ስለሚጣራበት አግባብ የሚመለከት ነዉ፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በኦሮሚያ ክልል በሰበታ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪ በአመልካች ላይ በመሰረቱት ክስ - ከአመልካች ጋር በጋብቻ ዉስጥ በነበሩበት ጊዜ ያፈሩት ንብረቶች እንደሆነ እና ጋብቻቸዉ መፍረሱን በመግለጽ የተለያዩ ንብረቶችን በመዘርዘር ድርሻቸዉ ተካፍሎ እንዲሰጣቸዉ የጠየቁ ሲሆን ከነዚህ ዉስጥ በፊት አዲስ አበባ ከተማ ስር ኮዬ ፈጬ ሳይት የነበረ አሁን ላይ በሸገር ከተማ በገላን ክፍለ ከተማ ኮዬ ፈጬ ሳይት ፕሮጀክት 16፣ ብሎክ 34፣ 6ኛ ፎቅ የሚገኝ፣የቤት ቁጥር 56 ባለ ሶስት መኝታ በአመልካች ስም የተሰጠና ብር 1,500,000.00 የሚያወጣ ስላለን እኩል እንድታካፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች በሰጡት መልስ - ሌሎች የመሬት ይዞታዎችና ቤት ወይም ንብረት የግል እንጂ ከተጠሪ ጋር በጋራ ያፈሩት እንዳልሆነ በመግለጽ ኮንዶሚኒዬም ቤቱም ይዞታቸው ለልማት ለተወሰደባቸው አርሶ አደሮች መንግስት በካሳ መልክ ሲሰጥ የእኔም ወላጆች አርሶ አደር ስለሆኑ በቤተሰብ አባልነቴ በዚህ አግባብ የተሰጠኝ ነው እንጂ ከተጠሪ ጋር አብረን ያፈራነው አይደለም፡፡ የቤት ዕቃዎችን በተመለከተ የጋራ ስለሆነ ብንካፈል ቅሬታ የለኝም በማለት ተከራክረዋል፡፡ እንዲሁም ባቀረቡት የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ተጠሪ ባቀረቡት የንብረት ዝርዝር ዉስጥ ሳይጠቅሱ የቀሯቸዉ መሬቶችና ንብረቶች ናቸዉ ያሏቸዉን በመዘርዝር ተጠሪ እኩል እንዲያካፍላቸዉ እንዲወሰን ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ተጠሪ ለተከሳሽ ከሳሽነቱ ክስ በሰጡት መልስ በጋብቻ ዉስጥ የተፈሩ የጋራ ንብረቶች በእጃቸዉ እንደሌለ በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ማስረጃ መዝኖ አዲስ አበባ ከተማ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ወረዳ 1 ልዩ ቦታው ናሆም አደባባይ የሚባል የሚገኝ 5 ክፍል ሰርቪስ ቤት፣1 ክፍል ሱቅ፣የመብራት ወፍጮ ቤት KV50 ያለው ላይ እና ቆርቆሮ በቆርቆሮ የተሰራ የጋራ ንብረት መሆኑ ስለተረጋገጠ በአይነት ወይም የቀረበው ግምት እኩል ይካፈሉ፡፡ኮንዶሚኒየም ቤቱን በተመለከተ ግራቀኙ አብረው ሲኖሩ ለአመልካች የተሰጠ መሆኑን አመልካች አምነዉ ተከራክረዋል፡፡ቤቱን ከመንግስት አግኝቼ ነው ቢሉም በማስረጃ አላረጋገጡም፡፡በማስረጃ የተረጋገጠ ቢሆን እንኳን በጋብቻ ውስጥ በአንድ ተጋቢ ስም የተገኘ ንብረት ሌላ ስምምነት ከሌለ በስተቀር የጋራ ንብረት እንደሚሆን የኦሮሚያ ቤተሰብ ሕግ አንቀፅ 78/3 ላይ ተደንግጓል፡፡ስለሆነም በአሁን ሰአት ኮዬ ፈጬ ገላን ከተማ ስር የሚገኘው ኮንዶሚኒየም ቤት የጋብቻ ንብረት ስለሆነ በጋራ ይካፈሉ፡፡በሰበታ ከተማ ቀበሌ 04 ዴርቱ የሚባል አካባቢ የሚገኝ መሬት መኖሩን በማስረጃ ስላላስረዳ ተጠሪ ከዚህ ረገድ ያቀረበው ጥያቄ ውድቅ ነው፡፡የተከሳሽ ከሳሽነት ክሱን በተመለከተ አብዲ ቦሩ የሚባል ማኅበር ውስጥ በተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ የመኖሪያ ቤት አለመኖሩ በመረጋገጡ የአመልካች ጥያቄ ውድቅ ሆኗል፡፡እንዲሁም አመልካች ተጠሪ የመኖሪያ ቤቱን ሸጧል በማለት ያቀረቡትን በተመለከተ ስልጣን ባለው አካል የሌለ መሆኑ በመረጋገጡ እና አመልካችም ቤቱ መኖሩን ያላስረዱ ስለሆነ ውድቅ ተደርጓል፡፡ሞተሩን በተመለከተ ተጠሪ በትዳር ውስጥ እያሉ መግዛቱን አምኖ ነገር ግን በትደር ውስጥ ነው የሸጥኩት ሲል ተከራክረዋል፡፡የባልና ሚስት የጋራ ተንቀሳቃሽ ንብረት ዋጋው ከ500 ብር በላይ የሚያወጣ ለመሸጥ የተጋቢዎች መተማመኛ አስላጊ እንደሆነ በኦሮሚያ ቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 84 ስር ተደንግጓል፡፡ስለሆነም የሰሌዳ ቁጥሩ 02-01-3939 የሆነው ሞተር የአመልካች እና ተጠሪ የጋራ ንብረት በመሆኑ ግማሹን ማለትም ብር 11,000 ተጠሪ ይክፈላቸዉ ሲል ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለሸገር ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ይግባኙን በመ/ቁጥር 51852 ላይ በቀን 26/10/2015 ዓ.ም በሰጠዉ ትእዛዝ ይግባኙን ሰርዞባቸዋል፡፡በመቀጠልም ይግባኝ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤትም በመ/ቁጥር 413871 ላይ በቀን 01/02/2016 ዓ.ም በሠጠዉ ትእዛዝ ሰርዞባቸዋል፡፡አመልካች ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡትን የሰበር

አቤቱታ ተቀብሎ በመ/ቁጥር 436731 ላይ አከራክሮ በቀን 27/02/2016 ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ጉድለት የለበትም ሲል አፅንቶታል፡፡

አመልካች ለዚህ ችሎት በቀን 05/03/2016 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ከላይ በተገለፀው መልኩ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈፀሞበታል በማለት ሲሆን ካቀረቧቸዉ በርካታ የቅሬታ ነጥቦች መካከል በጭብጥነት ተይዞ ያስቀርባል የተባለዉ ይዘት በአጭሩ - የኮንዶሚኒዬም ቤቱ የተሰጠኝ የወላጆቼ የእርሻ ይዞታ በልማት ምክንያት ስለተወሰደባቸው ሌላ የገቢ ምንጭ ወይም መተዳደሪያ ስለሌለኝ ሜዳ ላይ እንዳልወድቅ እንድተዳደርበት መተዳደሪያ ስለአጣሁ ለልማት ተነሺ የገበሬ ልጆች በሚል የተሰጠኝ እንጂ ተመዝግቤ፤ዕጣ ወጥቶልኝ ወይም ተዋውዬ ለጋራ የተሰጠን ስላልሆነ አንድላይ እያላችሁ የተሰጠ ስለሆነ የጋራ ነውና ለሁለት ተካፈሉ መባሉ የሕግ አግባብነት የሌለዉና በኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 25፣ 35/7 እና 40/2 ላይ የተደነገገዉን የሚጥስ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ተብሎ ይታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

ችሎቱም አቤቱታዉን መርምሮ አመልካች በስር ፍርድ ቤት በኮንደሚኒየም ቤቱ የልማት ተነሺ የገበሬ ልጅ በመሆን ያገኙሁት ስለሆነ ከተጠሪ ጋር ልካፈል አይገባም በማለት ያቀረቡት ክርክር ተገቢውን ጭብጥ ተይዞ ተጣርቶ መወሰን አለመወሰኑን በሰ/መ/ቁጥር 237381 ላይ ከተሰጠዉ የሕግ ትርጉም ጋር በማገናዘብ እንዲመረመር ተጠሪ መልስ እንዲሰጡ አዝዟል፡፡ተጠሪ በአድራሻቸው ባለመገኘታቸዉ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥሪ የተደረገላቸው ቢሆንም ቀርበው መልስ ያልሰጡ በመሆኑ መልስ የማቅረብ መብታቸው ታልፏል፡፡

ከላይ አጠር ባለ መልኩ የተገለጸዉ በክልሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች እንዲሁም የግራ ቀኙን ክርክር የሚመለከት ሲሆን እኛም ከፍ ሲል የተያዘዉን ጭብጥ መሠረት በማድረግ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የሕግ ስህተት መፈጸም አለመፈጸሙን እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

በተሻሻለው በፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 መሠረትም ሆነ በዚህ ጉዳይ ተፈጻሚነት ባለዉ በኦሮሚያ ክልል በተሻሻለዉ የቤተሰብ ሕግ መሠረት የተመሰረተ ጋብቻ ከሚያስከትላቸው ሕጋዊ ውጤቶች ውስጥ አንዱ በተጋቢዎቹ መካከል የጋራ የንብረት ባለቤትነትን (Communality of Property/ ማቋቋም ነዉ፡፡ በዚሁ አግባብ ባልና ሚስት ጋብቻቸዉን በሚፈጽሙበት ጊዜ በየግል የነበራቸዉ ንብረቶች ወይም ከጋብቻ በኋላ በዉርስ ወይም በስጦታ በየግላቸዉ ካገኙዋቸዉ ንብረቶች በስተቀር ተጋቢዎች ጋብቻቸውን ከፈፀሙበት ቀን ጀምሮ ባልና ሚስት ከግል ጥረታቸዉና ከግል ወይም ከጋራ ንብረታቸዉ የሚያገኟቸዉ ገቢዎች ዉጤቶች ሁሉ ፤በፍርድ የአንደኛዉ ተጋቢ የግል ሀብት ነዉ ተብሎ እስካልተወሰነ ድረስ ባልና ሚስት ከተጋቡ በኋላ በግብይት የሚያገኙት ንብረት ሁሉ፤ በስጦታ ዉል ወይም በኑዛዜ ላይ ለአንደኛዉ ተጋቢ የተሰጠ እንደሆነ በግልጽ ካልተመለከተ በስተቀር በጋብቻ ዉስጥ በስጦታ ወይም በኑዛዜ ለተጋቢዎቹ የተሰጧቸዉ ንብረቶች ሁሉ የጋራ ሀብቶቻቸዉ እንደሚሆኑ በክልሉ ቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 73

እና 78 ላይ ተደንግጓል፡፡በፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 57 እና 62 በተመሳሳይ ተመልክቷል፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች መሠረት በንብረት ረገድ የተወሰደው የሕግ ግምት መነሻው ተጋቢዎች የአስተዋጽዋቸው ደረጃ የተለያየ ቢሆንም በጋብቻ ውስጥ በሚፈራው ንብረት መገኘት ላይ እንደአቅማቸው እና ገቢያቸው መጠን የየራሳቸው የዓይነትም ሆነ የአገልግሎት አበርክቶ ይኖራቸዋል በሚል እና ንብረቱም በዚሁ አኳኋን የተፈራ እንደሚሆን በመቁጠር የጋራ ሀብት ባለቤትነት መብት በማቋቋም ለንብረት መብት ጥበቃ በማድረግ የጋብቻዉን ሰላማዊነትና ቀጣይነት ለማረጋገጥ ነዉ፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ኮንዶሚኒየም ቤት ግራ ቀኙ በጋብቻ ግንኙነት ዉስጥ በነበሩበት ጊዜ የተገኘ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ አመልካች ከስር ፍርድ ቤት ጀምሮ እስከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ አጥብቀው የሚከራከሩት "ቤቱ ቀደም ሲል ከወላጆቼ ላይ ያለበቂ ካሳ ለተወሰደባቸው የመሬት ይዞታ ምትክ የአርሶ አደር ልጅ በመሆኔ ምክንያት በካሳ መልክ የተሰጠኝ እንጂ ከተጠሪ ጋር በጋብቻ ዉስጥ ሆኜ የኮንዶሚኒየም ቤት ተመዝግቤ እጣ ወጥቶልኝ ያፈራነው ባለመሆኑ የጋራ ሀብት ሊባል አይገባም፡፡"በሚል ነው፡፡ ተጠሪ ለስር ፍርድ ቤት ባሰሙት ክርክር ኮንዶሚኒየም ቤቱ አመልካች የአርሶ አደር ልጅ በመሆናቸዉ መነሻነት የተገኘ መሆኑን ሳይክዱ በጋብቻ ውስጥ የተገኘ በመሆኑ የጋራ ሊባል ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡የክልሉ ፍርድ ቤቶችም ኮንዶሚኒየም ቤቱ አመልካች የአርሶ አደር ልጅ በመሆናቸዉ በአመልካች ስም የተሰጠ ቢሆንም በጋብቻ ውስጥ በአንዱ ተጋቢ ስም የተገኘ ንብረት ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ የጋራ ንብረት እንደሚሆን በኦሮሚያ ቤተሰብ ሕግ አንቀፅ 78/3 መሠረት የጋራ ሀብት ስለሚሆን ኮንዶሚኒየም ቤቱ ለግራ ቀኙ የጋራ ሀብት ነዉ በማለት ወስነዋል፡፡

ሆኖም የክልሉ ፍርድ ቤቶች ለዉሳኔዉ መሠረት ያደረጉት የክልሉ ቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 78/3 በጋብቻ ዉስጥ በስጦታ ወይም በኑዛዜ ለአንደኛዉ ተጋቢ የተሰጠ ንብረት በስጦታ ዉሉ ላይ በተቃራኒዉ በግልጽ ካልተመለከተ ንብረቱ ለተጋቢዎቹ የጋራ ሀብት ይሆናል በሚል የተደነገገበት ነዉ፡፡በተያዘዉ ጉዳይ አከራካሪዉ ኮንዶሚኒየም ቤት በስጦታ ወይም በኑዛዜ የተገኘ ነዉ የሚል ክርክር አልቀረበም፡፡የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከዚህ ጉዳይ ጋር ተመሳሳይ በሆነ ጉዳይ በሰ/መ/ቁጥር 237381 ላይ በቀን 30/02/2016ዓ.ም በዋለዉ ችሎት በአብላጫ ድምጽ *"በልማት ምክንያት ከይዞታቸው ለተፈናቀሉ ተገኚ አርሶ አደሮችና ቤተቦቻቸው የጋራ መኖሪያ ቤቶች/የኮንዶሚኒየም/ አሰጣጥን አስመልክቶ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን የወጣውን መመሪያ ቁጥር 003/2011"* እና የቤተሰብ ሕግ ድንጋጌዎችን በመጥቀስ በሰጠዉ ፍርድ ላይ *አንደኛው ተጋቢ የአርሶ አደር ልጅ በመሆኑ ምክንያት የአርሶ አደር ልጅ ከሌላ ሰዉ ጋር በጋብቻ ውስጥ እያለ የሚሰጠዉ ቤት እንደ ካሣ እንደሚቆጠርና ቤቱም ካሣ የተሰጠዉ ተጋቢ የግል ንብረት ተደርጎ ይቆጠራል እንጂ የተጋቢዎቹ የጋራ ሀብት ተደርጎ ሊቆጠር እንደማይገባ* አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡በመሆኑም በዚህ መልኩ በተሰጠዉ ትርጉም መሠረት በተገለጸዉ መሠረት በጋብቻ ዉስጥ ለአንደኛዉ ተጋቢ የተሰጠዉ ቤት እንደካሣ የሚቆጠር እንጂ

በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 78/3 ስር በተደነገገዉ መሠረት በስጦታ ወይም በኑዛዜ እንደተገኘ ሀብት የሚቆጠር ባለመሆኑ ይህ ድንጋጌ ለተያዘዉ አይነት ጉዳይ ተፈጻሚነት የለዉም፡፡

በያዝነዉም ጉዳይ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ኮንዶሚኒየም ቤት የተገኘው አመልካች የልማት ተነሺ አርሶ አደር ልጅ በመሆናቸዉ ምክንያት ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ተጠሪ ቤቱ በጋብቻ ዉስጥ የተገኘ በመሆኑ የጋራ ሊባል ይገባል በማለት ከሚከራከሩ በቀር በራሳቸውም የተነሺ የልማት ተፈናቃይ አርሶ አደር ልጅ ሆነው ቤቱ በአሁን አመልካች በኩል ብቻ እንዲገኝ የተደረገ ስለመሆኑ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ በእርግጥ ተጠሪ በራሳቸውም የአርሶ አደር ልጅ ቢሆኑ ኖሩ ሁለት እጣ ማንሳት ስለማይቻል በአመልካች ስም አንድ ቤት ብቻ ሊሰጠን ችሏል በሚል ይከራከሩ የነበረ ቢሆንም በዚህ መልክ ለስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክርክር ስለመኖሩ የስር ፍርድ ቤት የዉሳኔ ግልባጭ አያሳይም፡፡እንዲሁም ኮንዶሚኒየም ቤቱን የጋራ ሊያደርግ የሚችል በጋብቻ ዉስጥ በተጠሪ የተደረገ አስተዋጽኦ ስለመኖሩ አልያም በግራ ቀኙ መካከል ቤቱን የጋራ ለማድረግ የተደረገ ስምምነት ስለመኖሩ በማስረዳት በተጠሪ የቀረበ ክርክር የለም፡፡

ሲጠቃለል ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ኮንዶሚኒየም ቤቱ ግራ ቀኙ በጋብቻ ግንኙነት ዉስጥ እያሉ የተሰጠ ቢሆንም ለአመልካች በካሣ መልክ የተሰጠ በመሆኑ የአመልካች የግል ንብረት ነዉ፡፡ስለሆነም የክልሉ ፍርድ ቤቶች ለአመልካች በካሣ መልክ የተሠጠዉ ኮንዶሚኒየም ቤት በጋብቻ ዉስጥ የተገኘ በመሆኑ ብቻ ለግራ ቀኙ የጋራ ሀብት ይሆናል በሚል የሰጡት ዉሳኔ በሰ/መ/ቁጥር 237381 ላይ የተሰጠዉን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሚቃረን በመሆኑ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሸ) እና 10(1/ሐ) መሠረት ሊታረም የሚገባዉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ዉሳኔ</u>

1. የሰበታ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 22291 ላይ በቀን 01/10/2015 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ፣የሸገር ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 51852 ላይ በቀን 26/10/2015 ዓ.ም የሰጠዉ ትእዛዝ፣ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 413871 ላይ በቀን 01/02/2016 ዓ.ም የሠጠዉ ትእዛዝ እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 436731 ላይ በቀን 27/02/2016 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 መሠረት ተሻሽለዋል፡፡

2. በሸገር ከተማ በገላን ክፍለ ከተማ ኮዬ ፈጬ ሳይት ፕሮጀክት 16፣ ብሎክ 34፣ 6ኛ ፎቅ የሚገኝ፣ የቤት ቁጥር 56 የሆነ ባለ ሶስት መኝታ ኮንዶሚኒየም ቤት የአመልካች የግል ንብረት ነዉ ፡፡ሌላዉ የክልሉ ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ይዘት አልተነካም፡፡

3. በዚህ ችሎት ለነበረዉ ክርክር የወጣዉን ወጭ ግራ ቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

## ትእዛዝ

1. በዉሳኔዉ መሠረት እንዲያስፈጽም የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለስር ወረዳ ፍርድ ቤት ይተላለፍ። ግራ ቀኙ ሲጠይቁ ግልባጩ ይሰጣቸዉ።
2. የፍርድ አፈጻጸም እንዲታገድ የተሰጠዉ ትእዛዝ ተነስቷል፤ እንዲያዉቀዉ ለፍርድ ቤቱ ይሄዉ ተገልጾ ይጻፍ።
3. ዉሳኔዉ በቀን 07/06/2017 ዓ/ም ተነብቦ መዝገቡ ተዝግቷል ፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

መ/ዐ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ/254987

ጥር 26 ቀን 2017ዓ/ም

ዳኞች፡-ገበየሁ ፈለቀ

ደረጀ አያና

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

ብርሃኑ መንግሥቱ

አመልካች፡- ወ/ሮ ቀመሪያ ሁሴን ቀርቧል

ተጠሪ፡- ሼህ ጀማል ሁሴን አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በተጀመረበት በጋምቤላ ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ማጃንግ ዞን ጎደሬ ወረዳ ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ በተከሳሽነት ተከራካረዋል፡፡ አመልካች ባቀረቡት ክስ ከተጠሪ ጋር የነበራቸው ጋብቻ በፍርድ ቤት የፍቺ ውሳኔ መፍረሱን ተከትሎ ባቀረቡት የፍቺ ውጤት በሆነው የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍል አቤቱታ የጋራ ናቸው ካሏቸው ንብረቶች ውስጥ ለሰበር አቤቱታው ምክንያት የሆኑት በአቤቱታው ተራ ቁጥር 5 ሥር የተጠቀሰው በቶሊና ቶካሊ ቀበሌ ውስጥ የሚገኝ በ15 ቅጠል ቆርቆሮ ቤት ከንሮ አትክልቶች ያሉት እና ለቤት መሥሪያ የተዘጋጁ 100 ፍልጦች፤እንዲሁም በተራ ቁጥር 7 ከላይ በተጠቀሰው ቀበሌ ውስጥ የሚገኝ አዋሳኞቹ በክሱ ላይ የተመለከተው የቡና እና የባህር ዛፍ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

አትክልቶች እና ልዩ እንጨቶች ያሉበት ይዞታ የግራ ቀኙ የጋራ መሆኑን ገልጸው ተጠሪ ድርሻዬን ያካፍሉኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መልስ በተራ ቁጥር 5 የተጠቀሰውን ንብረት ከሟች እናታቸው በውርስ ያገኙት ሆኖ በንብረቱ ላይ በአመልካች በኩል የተደረገ እድሳት አለመኖሩን፤በተራ ቁጥር 7 የተጠቀሰው ይዞታም ታህሳስ 6 ቀን 1983 ዓ.ም በተደረገ የስጦታ ውል ከሟች እናታቸው ያገኙት እንጂ ከአመልካች ጋር በጋራ ያፈሩት ባለመሆኑ አከራካሪዎቹ ንብረቶች የግላቸው መሆኑን ተከራክረዋል፡፡

የጎደሬ ወረዳ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ በሰጠው ውሳኔ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40/3 የገጠርም ሆነ የከተማ መሬት የባለቤትነት መብት የመንግስትና የህዝብ እንደሆነ ስለሚደነግግ የመሬት ባለቤትነት ለግለሰብ አልተሰጠም፡፡ በክልሉ የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 45/1፣65/3 እና 66/1 ድንጋጌዎች እንደሚያመለክቱት ተጋቢዎች ጋብቻቸውን ከመፈጸማቸው በፊት ያፈሯቸውን ንብረቶች **በውል መወሰን ያለባቸው** መሆኑን፣በስጦታ ወይም በኑዛዜው በሌላ አኳኋን ካልተመለከተ በስተቀር በኑዛዜ ወይም በስጦታ ለተጋቢዎች የሚተላለፉ ንብረቶች የጋራ ሃብት ስለሆኑ ንብረቶቹ የግሌ ናቸው የሚለው ተጋቢ የግል ሀብቱ መሆኑን ካላስረዳ በቀር ንብረቱ በአንደኛው ተጋቢ ስም የተመዘገበ ቢሆን እንኳን የጋራ ሀብት ከመሆን የሚያስቀር አይደለም፡፡ ተጠሪ አከራካሪዎቹን ንብረቶች ከሟች እናታቸው በስጦታ እና በውርስ ያገኙ መሆኑ በግራ ቀኙ ማስረጃ የተረጋገጠ ቢሆንም ሟች እናታቸው በህይወት እያሉ እና ከሞቱ በኋላ በውርስና በስጦታ ያገኙትን ንብረት በቤተሰብ ህጉ በተመለከተው አግባብ አመልካችን በሚያገቡበት ጊዜ በጋብቻ ውል የግላቸው እንዲባል አላደረጉም፡፡ ይህ ባልሆነበት ተጠሪ አከራካሪዎቹን ንብረቶች ከሟች እናታቸው በውርስና በስጦታ ማግኘታቸው በአመልካች እና በተጠሪ ማስረጃዎች የተረጋገጠ ቢሆንም በህጉ አግባብ የግላቸው ስላላስባሉ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ነው በማለት ውስኗል፡፡

ተጠሪ አከራካሪዎቹ ንብረቶች በጋብቻ ውል የግላቸው ነው ተብለው ባይመዘገቡም የግላቸው መሆኑን ከአመልካች በተሸለ ሁኔታ ማስረዳት እስከቻሉ ድረስ የግላቸው ተብሎ ሊወሰን ሲገባው በጋብቻ ውል የግል ነው ተብሎ አልተመዘገበም በሚል የጋራ ነው ተብሎ መወሰኑ ህጉን በአግባቡ ተረድቶ ያለመተርጎም እንጅ ማስረጃን የሚመለከት ጉዳይ አይደለም በማለት ለማጀንግ ብሔረሰብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታ ያቀረቡ ቢሆንም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተጠሪን አቤቱታ ባለመቀበል የሥር የጎደሬ ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔን በማጽናቱ ተጠሪ ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ጉዳዩን የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት ባልና ሚስት ጋብቻ በሚፈጽሙበት ጊዜ በግል የነበሯቸው ንብረት፤እንዲሁም በትዳር ውስጥ እያሉ በውርስ ወይም በስጦታ በግል ያገኟቸው ንብረቶች የግላቸው ሆኖ እንደሚቀሩ የክልሉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 68/2000 አንቀጽ 60 መደንገጉን ጠቅሶ በተራ ቁጥር 5 እና 7 ሥር የተጠቀሱ ንብረቶችን ተጠሪ ከእናታቸው

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ወ/ሮ ሀሞና አባቡልጉ ታህሳስ 6 ቀን 1983 ዓ.ም በሥጦታ ያገኙ መሆኑ በሰው እና ሰነድ ማስረጃ በተሻለ መልኩ ተረጋግጦ እያለ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ተብሎ መወሰኑ የክልሉን የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 68/2000 አንቀጽ 60 ድንጋጌን ስለሚቃረን የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል አከራካሪዎቹ በተራ ቁጥር 5 እና 7 ሥር የተመለከቱ ንብረቶች የተጠሪ የግል ንብረት ናቸው በማለት ወስኗል፡፡

የሰበር ቅሬታው የቀረበው የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት በሰበር ለማሳረም ሆኖ የሰበር ቅሬታው ይዘት በአጭሩ፡- ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤትም ሆነ አትክልት መቼ ፤ በማን እና እንዴት እንደተፈራ በማስረጃ የሚጣራ የፍሬ ነገር ክርክር ሲሆን የሥር ፍርድ ቤቶች በማስረጃ አጣርተው የሰጡትን ውሳኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከተቋቋመለት ዓላማ ውጪ በመውጣት ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ሳይኖረው የሥር ፍርድ ቤቶች በማስረጃ አንጥረው የሰጡትን ውሳኔ መሻሩ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡ አመልካችና ተጠሪ ትዳር ስንመሰርት በየግላችን ምንም ያልነበረን ለወደፊት ሰርተን እናገኛለን በሚል ተስፋ ተጋብተን ለክርክር ምክንያት የሆኑ ንብረቶችን አፍርተን እያለ ታህሣሥ 6 ቀን 1983 ዓ.ም እናቴ በስጦታ አስተላልፋልኛለች በማለት ተጠሪ የሚከራከሩበት ማሳ ስጦታው በሐሰት የተዘጋጀ እና የስጦታ ሕግን የማያሟላ ከመሆኑም ባሻገር አከራካሪውን ይዞታ አመልካች እና ተጠሪ ባለፉት 35 ዓመታት ያለማነው የቡና እርሻ እንጂ አስቀድሞ ቡናም ሆነ ሌሎች አትክልቶች ያልነበሩበት ሲሆን ይህ ቡና ያለማንበት መሬት ደግሞ የሕዝብና የመንግሥት እንጂ የግል ሀብት አይደለም፡፡ በተራ ቁጥር 7 ላይ የተገለጸውን ቤትም አመልካችና ተጠሪ በጋብቻ ውስጥ እያለን በ2000 ዓ.ም ቦታው ከሚጢ ከተማ ማዘጋጃ ቤት በምሪት ተሰጥቶን በ2003 ዓ.ም 5 ክፍል ሰርቪስ ቤት በጋራ ሰርተን ዋናውን ቤት ለመሥራት እንጨት አስፈልጠን በዝግጅት ላይ የነበርን እንጂ ተጠሪ ከጋብቻ በፊት ያፈሩት ሀብት እንዳልሆነ አመልካች በሰውና በሰነድ ማስረጃ ያስረዱትን ተጠሪ ማስተባበል ካለመቻላቸውም በላይ የግል ይባልልኝ ብለው በፍርድ ቤት ባላስመዘገቡበት አከራካሪው ቤት የግላቸው ሊያደርገው የሚችል የሕግ መሠረት በሌለበት ሰበር ሰሚ ችሎቱ እነዚህ ንብረቶች የተጠሪ የግል ናቸው ማለቱ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 6/1 መሠረት ለሰበር ሰሚው ችሎቱ የተመራው የሰበር አቤቱታ በሰበር ሰሚ ችሎቱ ተመርምሮ የጋምቤላ ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት ተጠሪ ለሰበር ክርክሩ መነሻ ምክንያት የሆኑት በክስ አቤቱታው በተራ ቁጥር 5 እና 7 ላይ የተጠቀሱት ንብረቶችን እንደቅደም ተከተላቸው ከእናታቸው በውርስ እና ስጦታ ያገኙ ስለመሆናቸው ከአመልካች በተሸለ ሁኔታ በማስረጃ ስላረጋገጡ ንብረቶቹ ከአመልካች ጋር በጋራ የተፈሩ አይደሉም በማለት የሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ከአዋጅ ቁጥር 1234/2013 ቁጥር 2/4(ለ) እና (ሸ) አንፃር ለማጣራት ሲባል ያስቀርባል በማለቱ ተጠሪ

ጥሪ ተደርጎላቸው በሰጡት መልስ፡- የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ለክርክር መነሻ የሆኑት ንብረቶች የተጠሪ የግል ንበረቶች ናቸው ሲል ውሳኔ የሰጠው የስር ፍርድ ቤቶች የቀረበውን የሰውና የሰነድ ማስረጃ የመዘኑበት አግባብ የማስረጃ ምዘና መርህን የጣሰ እና የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በሚል ነው፡፡ አመልካችና ተጠሪ ስንጋባ ምንም አልነበረነም፤ ለክርክሩ ምክንያት የሆኑት ንብረቶችን ከትዳር በኋላ በጋራ ጥረት አፍርተናል የሚል ክርክር በስር ፍርድ ቤቶች አላቀረቡም፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክርክር አብረን ገንብተን አልምተናል በሚል ነው፡፡ ጠፍ መሬት አግኝተን አልምተናል በማለት ያቀረቡት ክርክርም ሀሰት ነው፡፡ ተጠሪ ያቀረበው የስጦታ ውል በሀሰት የተዘጋጀ እና ህግን መሰረት ያላደረገ ነው የሚለው ክርክርም በስር ፍርድ ቤት ያልተነሳ አዲስ ክርክር በሰበር መቅረቡ ሥነ ሥርዓታዊ ባለመሆኑ ውደቅ ነው፡፡ አከራካሪው የቡና መሬት የሟች እናቴ የነበረ ሆኖ ታህሳስ 6 ቀን 1983 ዓ.ም እንደሰጠችኝ እና ለጅም ዓመታት ከአመልካች ጋር ስንኖር በአላባው ከመጠቀም ውጭ ምንም አይነት እድሳት ወይም የተተከለ አትክልት አለመኖሩን በውሉ ላይ እማኝ የነበሩ ሰዎች በተመሳሳይ ቃል የሰጡት ምስክርነት በአመልካች ምስክሮች ጭምር ተቀባይነት ያገኘ በመሆኑ አመልካች ከተጠሪ ጋር ረጅም ዓመታት ቆይቻለሁኝ በሚል መነሻ ያልነፋችበትን ንብረት ለማግኘት የሚታቀርበው የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም፡፡ በክሱ በ7ኛ ተራቁጥር የተጠቀሰው በሜጢ ከተማ የሚገኘው ሰርቪስ ቤትም አመልካችን ሳላገባ የሰራሁት ሲሆን ትልቅ የመኖሪያ ቤት ለመስራት አስበን እንጨት አዘጋጅተን የነበረ ቢሆንም አመልካች በመሄዳቸው ምክንያት ልሰራ አልቻለም፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆኑት ንብረቶችን ተጠሪ በውርስና በስጦታ ያገኘኋቸው መሆኑ ስለተረጋገጠ ከማስረጃ ምዘና መርህ አንጻር የጋምቤላ ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ባለመኖሩ ለሰበር አቤቱታው መሠረት የሆነው ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራካረዋል፡፡

አመልካች ህዳር 30 ቀን 2017 ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ ክርክራቸው ተጠሪ አንዴ ንብረቱን ከጋብቻ በፊት ያፈራሁት ነው፤ሌላ ጊዜ ደግሞ ከእናቴ በሥጦታ ያገኘሁት ነው በማለት እውነቱን ማድበስበስ ቢሞክሩም እውነቱ ንብረቱ ግራ ቀኙ በጋብቻ ውስጥ እያሉ የተፈራ የጋራ ንብረት እንጅ ለተጠሪ ከሟች እናቱ በሥጦታ ወይም በውርስ የተላለፈለት አለመሆኑን ያመለክታል፡፡ የተጠሪ እናት በባልና ሚስቱን ተጠግተው በእነሱ ዕርዳታ ይኖሩ የነበሩ እንጅ በስማቸው የተፈራ ቋሚ ንብረት ያልነበራቸው መሆኑን ጠቅሰው የሰበር ሰሚ ችሎቱ ውሳኔ ተሽሮ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንዲፀናላቸው ጠይቀዋል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለ መልኩ የተመለከተው የግራ ቀኝ ክርክር እና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ውሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንፃር የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ንብረት ማፍራት መሠረታዊ መብት መሆኑና ማንኛውም ሰው በጉልበቱ ፣በመፍጠር ችሎታው ወይም በካፒታሉ ያፈራው ንብረት ባለቤት እንደሆነ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አዋጅ ቁጥር 1/1987 አንቀጽ 40/1 እና(2) ጣምራ ንባብ መረዳት ይቻላል፡፡ ሰቶች ንብረት የማፍራት፣ የማስተዳደር ፣የመቆጣጠር፣ የመጠቀምና የማስተላለፍ መብት ያላቸው መሆኑን አንቀጽ 35/2 ያስረዳናል፡፡ ባለሀብነት ከሁሉ የሰፋ መብት መሆኑንና በሕግ ካልተገደበ በቀር ባለሀብቱ ሀብቱን በፈለገው መንገድ ልገለገልበት የሚችል መሆኑን ከፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 1204 እና 1205 ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ባለሀብትነት በሕግ ወይንም ባለጉዳዮች በሚያደርጓቸው ሕጋዊያን ተግባሮች ሊተላለፍ መቻሉን፣ሀብትነቱ ለሌላ ሰው ስተላለፍ የቀደመው ሀብትነት ቀሪ እንደሚሆን ከፍትሐብሔር ሕጉ ቁጥር 1184 ፣1185 እና 1189 ድንጋጌ መረዳት ይቻላል። ንብረት በግል ወይም በጋራ ሊፈራ ይችላል፡፡ የባልና ሚስት የጋራ የንብረት ባለሀብትነት የሚፈጠረው በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 1258 ላይ እንደተመለከተው በጋራ ባለሀብቶች መካከል በሚደረግ ስምምነት ሳይሆን በሕግ ነው፡፡ Matrimonial property is created principally by operation of law, and not by will of parties unlike joint ownership property. Therefore, matrimonial property, unlike co-owership is statutory creation, applying exclusively to married couples as one of the effects of their matrimomial union. ይህ ማለት ግን ተጋቢዎች አስቀድሞ ወደ ትዳር ውስጥ ከመግባታቸው በፊት በግል የነበራቸውን ንብረት በጋብቻ ውል የጋራ ማድረግን አይከለክልም፡፡ ሌላው የባልና ሚስት ንብረት ከጋራ ባለሀብትነት የሚለየው ጋብቻ ፀንቶ እያለ ማንኛውም ተገቢ የንብረት ክፍፍል ጥያቄ ማቅረብ አይችልም፡፡ የጋራ ባለሀብቶች ቁጥር ከሁለት በላይ ሊሆን የሚችል ሲሆን በባልና ሚስት የጋራ ባለሀብትነት ግን በመርህ ደረጃ ቁጥሩ ከሁለት አይበልጥም፡፡

ጋብቻ ሕጋዊ ድርጊት (juridical act) በመሆኑ ሕጋዊ ውጤትን ያስከትላል፡፡ ጋብቻ የተፈፀመበት ሥርዓት ከግምት ሳይገባ ተመሳሳይ ወጤት አለው፡፡ ከጋብቻ ውጤቶች መካከል በውል ሊቀየሩ ወይም ሊሻሻሉ የሚችሉ ያሉ ቢሆንም በውል ሊቀየሩ ወይም ሊሻሻሉ የማይችሉ አስገዳጅ ውጤቶችም አሉ፡፡ ጋብቻ በግላዊ ግንኙነት ላይ ከሚኖረው ውጤት አንዱ መከባበር፣መተጋገዝና መደጋገፍ መሆኑን፣እንዲሁም ከንብረት አንፃር የሚያስከትለው ውጤት ተጠቃሾች መሆናቸው በተሸሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 49፣አንቀጽ 57 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ሥር ተመልክቷል፡፡

በተጋቢዎቹ እጅ ያሉ ንብረቶች በማን ስም ተመዘገቡ የሚለው ከግምት ውስጥ ሳይገባ የጋራ ሀብት እንደሆኑ ስለሚቆጠር የግል ንብረቴ ነው የሚል ተጋቢ የግሉ/ሏ መሆኑን የማስረዳት ግዴታ እንደለበት ወይንም እንደለባት አንቀጽ 63/1 ያመለክታል፡፡ ከተሻሻለው የቤተሰብ ሕጉ ቁጥር 62/1 መረዳት እንደሚቻለው ባልና ሚስት በግል ጥረታቸው የሚያፈሩት ንብረት የጋራቸው ነው፡፡ ባልና ሚስት ጋብቻቸውን በሚፈጽሙበት ጊዜ በየግል የነበራቸው ንብረቶች ወይም ከጋብቻ በኋላ በውርስ ወይም

በስጦታ በየግላቸው ያገኙዋቸው ንብረቶች የግል ቢሆኑም ከግል ሀብታቸው የሚገኙ ገቢዎች የጋራ ናቸው፡፡( የተሸሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 57 እና 62/1፤የጋምቤላ ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የበቴሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 68/2000 አንቀጽ 60 ይመለከቷል)፡፡

ይህ የሕጉ እሳቤ ጋብቻ በተጋቢዎቹ ግላዊ ግንኙነት ላይ ከሚያስከትላቸው ውጤቶች አንዱ በአንቀጽ 49/1 ሥር የተመለከተው የመተጋገዝና መደጋገፍ ግዴታ መኖር በባልና ሚስት ግንኙነት ውስጥ ከሚፈራው ንብረት ጀርባ የተጋቢዎቹ ጥረት ይኖራል በሚል ግምት መነሻነት ነው፡፡ በዚህ አግባብ በሚፈራው የጋራ ንብረት ላይ ባልና ሚስቱ እኩል መብት ያላቸው መሆኑን ከሕገ መንግስቱ አንቀጽ 34/2 እና የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 90 ድንጋጌ መረዳት ይቻላል፡፡ የግል ንብረት ዓይነቱን ለውጦ በተገኘ ጊዜ የግል ሆኖእንዲቀጥል በአንቀጽ 58/2 ሥር በተመለከተው አግባብ ማስገለል ያስፈልጋል፡፡

ጋብቻ በተጋቢዎቹ ግላዊ ግንኙነት እና ንብረት በኩል ሕጋዊ ውጤት የሚያስከትል በመሆኑ በፍቺ ውሳኔ ቀሪ ከሚሆኑት ውጪ ያለው ሕጋዊ ውጤት በተጋቢዎች ስምምነት ወይንም በፍርድ ቤት ውሳኔ የሚቋጭ ይሆናል፡፡ የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍልን አስመልክቶ ጋብቻ ሲፈፀም ወይንም በፍቺ ወቅት የተደረገ የሚፀና ሕጋዊ ውል በማይኖርበት ጊዜ የባልና ሚስት ንብረት ተጣርቶ የግል የሆነውን ባለንብረቱ የሚወስድ ሲሆን ፤ የጋራ የሆነው ንብረት በሕጉ አግባብ ባልና ሚስቱ እንዲካፈሉ የሚወሰን መሆኑን የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 85 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች የሚያመለክት ሲሆን የጋምቤላ ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 68/2000 ተመሳሳይ ድንጋጌ ሊኖረው እንደሚችል እሙን ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ የጎደሬ ወረዳ ፍርድ ቤት አከራካሪዎቹ በክሱ በተራ ቁጥር 5 እና 7 ሥር የተጠቀሱት ንብረቶችን ተጠሪ ከሚች እናታቸው በስጦታ እና በውርስ ያገኙ መሆኑ በግራ ቀኙ ማስረጃ ተረጋግጦ እያለ የባልና ሚስት የጋራ ሀብት ናቸው በማለት የወሰነው ተጠሪ ሟች እናታቸው ወ/ሮ ሀሞና አባቡልጉ በህይወት እያሉ በስጦታ ያገኙትን እና ከሞቱ በኋላ የወረሱትን ንብረት በቤተሰብ ህጉ በተመለከተው አግባብ አመልካችን በሚያገቡበት ጊዜ በጋብቻ ውል የግላቸው እንዲባል ኣላደረጉም በሚል ሲሆን ተጠሪ አከራካሪዎቹ ንብረቶች በጋብቻ ውል የግላቸው ነው ተብለው ባይመዘገቡም የግላቸው መሆኑን ከአመልካች በተሸለ ሁኔታ ማስረዳት እስከቻሉ ድረስ የግላቸው ተብሎ ሊወሰን ሲገባው በጋብቻ ውል የግል ነው ተብሎ አልተመዘገበም በሚል የጋራ ነው ተብሎ መወሰኑ ህጉን በአግባቡ ተረድቶ ያለመተርጎም እንጅ ማስረጃን የሚመለከት ጉዳይ አይደለም በማለት ለማጀንግ ብሔረሰብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታ ያቀረቡ ቢሆንም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተጠሪን አቤቱታ ባለመቀበል የሥር የጎደሬ ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔን በማጽናቱ ተጠሪ ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ጉዳዩን የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት ባልና ሚስት

ጋብቻ በሚፈጽሙበት ጊዜ በግል የነበራቸው ንብረት፣እንዲሁም በትዳር ውስጥ እያሉ በውርስ ወይም በስጦታ በግል ያገኟቸው ንብረቶች የግላቸው ሆኖ እንደሚቀሩ የክልሉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 68/2000 አንቀጽ 60 መደንገጉን ጠቅሶ በተራ ቁጥር 5 እና 7 ሥር የተጠቀሱ ንብረቶችን ተጠሪ ከእናታቸው ወ/ሮ ሀሞና አባቡልጉ ታህሳስ 6 ቀን 1983 ዓ.ም በሥጦታ ያገኙ መሆኑ በሰው እና ሰነድ ማስረጃ በተሻለ መልኩ ተረጋግጦ እያለ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ተብሎ መወሰኑ የክልሉን የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 68/2000 አንቀጽ 60 ድንጋጌን ይቃረናል በሚል የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔን ሽሯል፡፡ አመልካች ያቀረቡት የሰበር ቅሬታ ያስቀርባል የተባለው የጋምቤላ ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት ተጠሪ ለሰበር ክርክሩ መነሻ ምክንያት የሆኑት በክስ አቤቱታው በተራ ቁጥር 5 እና 7 ላይ የተጠቀሱት ንብረቶችን እንደቅደም ተከተላቸው ከእናታቸው በውርስ እና ስጦታ ያገኙ ስለመሆናቸው ከአመልካች በተሸለ ሁኔታ በማስረጃ ስላረጋገጡ ንብረቶቹ ከአመልካች ጋር በጋራ የተፈሩ አይደሉም በማለት የሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ለማጣራት ቢሆንም ተጠሪ አከራካሪዎቹን ንብረቶች ከእናታቸው በስጦታ እና በውርስ ከአመልካች ጋር ትዳር ከመመስረታቸው በፊት ያገኙ መሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር መሠረት አድርጎ የሥር ፍርድ ቤቶች ከጋብቻ በፊት የተፈራ ንብረት የግል መሆኑ በቤተሰብ ሕጉ በግልጽ ተመልክቶ እያለ በጋብቻ ውል የግል ተብሎ ስላልተመዘገበ የጋራ ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ የቤተሰብ ሕጉን ይቃረናል በሚል የስር የጋምቤላ ሕዝቦች ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት የወረዳ እና ዞን ፍርድ ቤቶችን ሰሩትን ስህተት ማረሙ አግባብ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍ ባለመሆኑ ቀጣዩ ተወስኗል፡፡

## ውሳኔ

1. የጋምቤላ ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 01332/2015 መስከረም 28 ቀን 2016 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ እና ውሳኔ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 9(1/ሀ) መሠረት **ፀንቷል፡፡**
2. በዚህ ችሎት የተደረገው ክርክር ላስከተለው ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ውሳኔ አግኝቶ ስለተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ፋ/ዘ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት**

የሰ/መ/ቁጥር፡- 255592

ጥር 26 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች፡-ገበየሁ ፈለቀ

አለማየሁ ሹናራ

ደረጀ አያና

ኑረዲን ከድር

ብርሃኑ መንግስቱ

አመልካች፡- አቶ ሰለሞን አርአያ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ/ ህፃን ዳንኤል ቴውድሮስ ሞግዚት ወ/ሮ የሺ መንግስቱ

2ኛ/ አቶ ሳሙኤል አርአያ

3ኛ/ ወ/ሮ ሮማን ለገሰ

4ኛ/ አቶ ሄኖክ አርአያ

5ኛ/ ወ/ሪት ሊዲያ አርአያ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

# ፍርድ

ጉዳዩ የውርስ ማጣራትን የሚመለከት ሆኖ አቤቱታው በቀረበበት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አመልካች 5ኛ ጣልቃ ገብ ፣ 2ኛ ተጠሪ የስር ተጠሪ፣1ኛ ተጠሪ የስር አመልካች፣ ከ3ኛ እስከ 5ኛ ያሉ ተጠሪዎች ደግሞ 3ኛ፣4ኛ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

እና 6ኛ ጣ/ገቦች ነበሩ፡፡ የክርክሩ አመጣጥ በአጭሩ፡- የአሁን 1ኛ ተጠሪ ባቀረቡት አቤቱታ የሟች ባለቤታቸው ቴውድሮስ አርአያ ወላጆች የልጃቸው አያት የሆኑት ጀነራል አርአያ ዘርዓይ ጥር 25 ቀን 2003 ዓም እናቱ ወ/ሮ ሰነዳይ ሀይሌ ጥር 04 ቀን 2004 ዓም ከዚህ አለም በሞት የተለዩ መሆኑን፤ባለቤታቸው ከወንድሞቹና እህቶቹ ጋር በመሆን በ29/08/2005 ዓም ወራሽነታቸውን ያረጋገጡ ቢሆንም ውርሱ ሳይጣራ መኖሪያ ቤቱን ሳይከፋፈሉ በጋራ ይዘው ሲጠቀሙበት ቆይተው ከ2006 ዓም ጀምሮ ቤቱን አከራይተው የኪራዩን ገንዘብ እኩል እየተካፈሉ መሆኑን ገልጠው ድርሻቸውን ለይተው ለማወቅና ለማረጋገጥ እንዲችሉ የውርስ ሀብት እንዲጣራ ጠይቀዋል፡፡

2ኛ ተጠሪ የውርሱ ሀብት እንዲጣራ ወራሽ መሆናቸውን ያረጋገጡት ወደ ክርክሩ እንዲገቡ ጠይቀው አመልካችና ከ3ኛ እስከ 5ኛ የተመለከቱት ተጠሪዎች ወደ ክርክሩ እንዲገቡ በስር ፍርድ ቤት የተፈቀደላቸው ሲሆን ውርሱ እንዲጣራ አጣሪ ተሹሞ አጣሪው ሪፖርቱን በ15/07/2015 ዓም አቅርቦ ከ5ኛ ተጠሪ ውጪ ያሉት ተከራካሪ ወገኖች አስተያየታቸውን አቅርበዋል፡፡ከዚህ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ተገቢውን ጭብጥ በመያዝ መዝገቡን መርምሮ በሰጠው ውሳኔም አመልካች የውርስ ሀብት የሆነው ቤት ተከራይቶ እስከዛሬ ምንም ድርሻ ደርሷቸው እንደማያውቅ በመግለፅ ድርሻቸው እንዲሰጣቸው የጠየቁ መሆኑን፤አመልካች ወራሽነታቸውን በ2005 ዓም ያረጋገጡ ቢሆንም በውርስ ሀብቱ ሲጠቀሙ እንዳልነበረ ካቀረቡት አቤቱታ ለመረዳት የሚቻል መሆኑን በመጥቀስ የአመልካች የወራሽነት መብት በፍ/ብ/ህ/ቁ.1000(1) መሰረት በሶስት አመት ይርጋ የታገደ ነው በማለት አቤቱታቸውን ውድቅ አድርጎ የሟች ጀነራል አርአያ ዘርዓ እና ወ/ሮ ሰንዳይ ሀይሌ ወራሾች በድምሩ አምስቱ ከውርስ ሀብቱ ላይ እየአንዳንዳቸው 1/5ኛ ድርሻ አላቸው በማለት ወስኗል፡፡አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ይግባኛቸውን ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ይግባኛቸውን በፍ/ብ/ስ/ስህ/ቁ.337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

የሰበር ቅሬታው በአጭሩ፡-አመልካች ከእህትና ከወንድሞቼ ጋር በመሆን ወራሽነቴን በ29/08/2005 ዓም ያረጋገጥኩ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን የፍ/ብ/ህ/ቁ.1000(1) በመጥቀስ፤ወራሽነቴ በመረጋገጡ በፍ/ብ/ህ/ቁ.1062 መሰረት የንብረት ክፍፍሉ ጥያቄ በማናቸውም ጊዜ ሊቀርብ እየቻለ ክሱ በይርጋ ይታገዳል ማለቱ በሰ/መ/ቁ.38533 የተሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሰረት ያደረገ አይደለም፡፡2ኛ ተጠሪ የቤቱን ኪራይ ለተጠሪዎች ሲያካፍል የነበረ መሆኑን፤የአመልካችም ድርሻ 2ኛ ተጠሪ ጋር እንደሚገኝ ለውርስ አጣሪው አረጋግጠው እያለ ለጉዳዩ አግባብነት የሌላቸውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም በመጥቀስ የአመልካች ወራሽነት በይርጋ የሚታገድ ነው በማለት መደምደሙ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ አመልካች የውርሱ ሀብት 1/6ኛ ይገባቸዋል ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

አቤቱታው የቀረበለት የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ለዚህ ችሎት ከመራው በኋላ ይህ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ፡ ጀነራል አርአያ ዘርዓይ ጥር 25 ቀን 2003 ዓም እናቱ ወ/ሮ ሰነዳይ ሀይሌ ጥር 04 ቀን 2004

ዓም ከዚህ አለም በሞት ተለይተው አመልካች ከሌሎች ወራሾች ጋር በመሆን ወራሽነታቸውን በ2005 ዓም አረጋግጠው እያለ፤ውርሱም የተለየ ከመሆኑ አኳያ የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች በውርስ ሀብቱ ሲጠቀም ስላልነበረ መብቱ በሶስት አመት ይርጋ ይታገዳል በማለት የመወሰናቸውን አግባብነት ለመመርመር ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ይቅረብ፡፡ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክራቸውን ይለዋወጡ በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

በዚህ አግባብ 1ኛ ተጠሪ ጥቅምት 25 ቀን 2017 ዓም በሰጡት መልስ በአመልካች ላይ ያቀረቡት የይርጋ መቃወሚያ አለመኖሩን ገልጸው አመልካች የውርስ ድርሻቸውን ቢካፈሉ የማይቃወሙ መሆኑን በመጥቀስ መልሳቸውን ያቀረቡ ሲሆን፤3ኛ፤4ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች በበኩላቸው ከውርስ ሀብቱ ቤት የኪራይ ገንዘብ ላይ እየአንዳንዳቸው 1/6ኛ የሚደርሳቸው መሆኑን ገልፀው መልስ ሰጥተዋል፡፡

2ኛ ተጠሪ ህዳር 04 ቀን 2017 ዓም በሰጡት መልስም አመልካች የውርስ ሀብቱ እንዲጣራ ሲጠይቁ ከውርስ ሀብቱ ከሚደርሰኝ ድርሻ ላይ 2ኛ ተጠሪ የውርስ ሀብቱን በመያዝ የሰበሰበው የኪራይ ገንዘብ ይመለስልኝ በማለት የጠየቁ ሲሆን ይህም ክሳቸው በቤቱ አለመጠቀማቸውን የሚያሳይ ሲሆን ይህም በሰ/መ/ቁ.44025 መሰረት መጠቀምን እንደመከራከሪያ ሊያነሱ የማይችሉ መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ፤በሰበር አስገዳጅ ውሳኔ መሰረት ውርስ በማጣራት ብቻ የበሰለ መብት ሳያረጋግጡ የይርጋው አቆጣጠር ሊቋረጥ እንደማይችል የወሰነ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካች ለ2ኛ ተጠሪ መልስ ህዳር 04 ቀን 2017 ዓም የተፃፈ የመልስ መልሳቸውን በማቅረብ ክርክራቸውን አጠናክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለፀውን ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ፣ ከጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እና ቅሬታው ለሰበር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ነጥብ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡በመሰረቱ ይርጋ ከሚያስከትለዉ ዉጤት አንፃር መብት የሚሰጥ(የሚያስገኝ) ይርጋ (acquisitive prescription) እና መብት የሚያሳጣ ይርጋ (extinctive prescription) በሚል የሚከፋፈል ሲሆን መብት የሚያሳጣ ይርጋን በተመለከተም ባለመብቱ (ባለገንዘቡ) በሕግ በተመለከተዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥ መብቱን (ጥቅሙን ወይም ገንዘቡን) ሳይጠይቅ ቆይቶ ጊዜዉ ካለፈበት መብቱን መጠየቅ እንዳይችል የሚያደርገውን (right killer limitation) የይርጋ አይነት የሚወክል መሆኑን፤ መብት የሚያሳጣ ይርጋ (extinctive prescription) መብት ለማስከበር የሚቀርብን ክስ ቀሪ የሚያደርግ (limitation of action)ይርጋን የሚያጠቃልል መሆኑን ከአጠቃላይ የሕጉ መርህ የምንረዳው ነው፡፡

የወራሽነት ክስ የውርስ ሀብቱ ወራሽ በሆነ እና ባልሆነ ሰው ሲያዝ የይርጋ ጊዜን ለይቶ ባለመቀመጡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የወራሽነት ክስን በተመለከተ በወራሾች መካከል የውርስ

ክፍፍል ጥያቄ በ3 ዓመት ይርጋ እንዲሁም ወራሽ እና ወራሽ ባልሆነ ሰው መካከል የውርስ ሀብት ይለቀቅልኝ ክስ ደግሞ 10 ዓመት ይርጋ የሚታገድ መሆኑን በሰበር በመዝገብ ቁጥር 52407፣ 20295፣ 30158፣ 34011፣25567 ፣25664፣26422 እና በሌሎችም በርካታ መዛግበት አስገዳጅ የህግ ትርጉም የተሰጠ በመሆኑ ውሳኔዎቹ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 መሰረት ለተያዘው ጉዳይም በተመሳሳይ ተፈጻሚነት ያላቸው በመሆናቸው አሁን የተያዘው የውርስ ሀብት ክርክር በወራሾች መካከል መሆኑ ለጉዳይ አግባብነት ያለው በፍ/ብ/ህ/ቁ.1000(1) የተመለከተው የሶስት አመት የይርጋ ጊዜ መሆኑን ከአጠቃላይ የአስገዳጅ የህግ ትርጉሞቹ ይዘት የምንረዳው ነው፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይ ጀነራል አርአያ ዘርዓይ ጥር 25 ቀን 2003 ዓም እናቱ ወ/ሮ ሰነዳይ ሀይሌ ጥር 04 ቀን 2004 ዓም ከዚህ አለም በሞት ተለይተው አመልካች የውርስ ሀብት ይገባኛል በማለት የጣልቃ ገብነት አቤቱታውን ያቀረቡት ሚያዚያ 24 ቀን 2015 ዓም መሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ.1000(1) የተመለከተው የሶስት አመት የይርጋ ጊዜ ካበቃ በኋላ የጣልቃ ገብነት አቤቱታው መቅረቡን የሚያሳይ ሲሆን፤አመልካች የወራሽነት ማስረጃ ሚያዚያ 29 ቀን 2005 ዓም ያወጡ መሆኑን በመግለጽ ክሱ በይርጋ ሊታገድ አይገባም በማለት ሰበር ሰሚ ችሎቱ በሰበር መዝገብ ቁጥር 38533፤44237 እና ሌሎች መዛግባት ላይ የሰጠውን ትርጉም መሠረት አድርገው መከራከራቸው እንዲሁም የውርስ ሀብት (የመኖሪያ ቤት) ሲጠቀሙ የቆዩ መሆኑን በመጥቀስ መከራከራቸው የአመልካች ክርክር ከይርጋ አቆጣጠር መቋረጥ ጋር የተያያዘ መሆኑን ያሳያል፡፡አመልካች ከይርጋ አቆጣጠር መቋረጥ ጋር በተያያዘ ያቀረቡትን የመጀመሪያ ምክንያት በተመለከተ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 996 እንደተመለከተው የኢትዮጵያ የውርስ ሕግ ከይዘት አንጻር በተመሳሳይ ሁኔታ በፍርድ ቤት የሚሰጠው የምስክር ወረቀት ወራሽነትንና ወራሽነቱ የተረጋገጠለት ሰው ከውርስ የሚያገኘውን ድርሻ የሚመለከት ቢሆንም በውጤት ደረጃ ግን ወራሽ ስለመሆን ግምት የሚያስወስድ ብቻ መሆኑን (የፍ/ሕ/ቁ. 997 ይመለከቷል) በሌላ አነጋገር የወራሽነት ማስረጃ መኖር ወራሽ ተደርጎ ከመገመት ባለፈ የንብረት መብት የማይፈጥር መሆኑን፤ ከንብረት የማስተላለፍ ስልት አኳያ ወራሾች ወዲያውኑ በውርስ ንብረቱ ላይ መብት እንደማይኖራቸው ግልጽ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ሕጉ የምስክር ወረቀቱ ማስረጃ ከንብረት ጋር በተያያዘ የሚፈጥረው መብት ስለመኖሩ የሚናገረው ነገር አለመኖሩን፤የይርጋ ድንጋጌ ይዘትም የሚያወራው ስለምስክር ወረቀቱ ሳይሆን ስለወራሽነት ጥያቄ (petitio hereditatis) መሆኑን መነሻ በማድረግ የወራሽነት ማስረጃ መያዝ አለመያዝ ልዩነት ሳይኖረው በተጠቀሰው የሶስት ዓመት ጊዜ ውስጥ የወራሽነት ጥያቄ ካልቀረበ ክሱ በይርጋ የሚታገድ መሆኑን በመጥቀስ የወራሽነት የምስክር ወረቀት ለያዘ ወራሽ ለዳኝነት ጥያቄው የጊዜ ገደብ የለውም በሚል በመ/ቁ. 205248 ፤44237፣38533 እና በተመሳሳይ መዝገቦች የተሰጡ የሰበር ውሳኔዎችን በመለወጥ በሰ/መ/ቁ.243973 በሰባት ዳኞች አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሰጠቱ አመልካች የወራሽነት ማስረጃውን ሚያዚያ ቀን 2005 ዓም ስላወጣሁ ክሴ በይርጋ ሊታገድ አይገባም በማለት ያቀረቡት ክርክር በሰ/መ/ቁ.243973 የተሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሰረት ያላደረገ መሆኑን ያሳያል፡፡

አመልካች ከይርጋው አቆጣጠር መቋረጥ ጋር በተያያዘ ያቀረቡትን ሁለተኛ ምክንያት በተመለከተ አመልካች ከመነሻውም ለአጣሪው አቤቱታቸውን ሲያቀርቡ የውርስ ሀብት የሆነው ቤት ተከራይቶ እስከዛሬ ምንም ድርሻ ደርሷቸው እንደማያውቅ በመግለፅ ድርሻቸው እንዲሰጣቸው በመጠየቅ የዳኝነት ጥያቄያቸውን ባቀረቡበት፤2ኛ ተጠሪ ከአመልካች ጋር በተደረገ ስምምነት ወይም በሌላ የሕግ አግባብ የአመልካችን የውርስ ሀብት የኪራይ ድርሻ እንዲቀበሉ የተደረገበት አግባብ ክርክር ቀርቦ በማስረጃ ባልተረጋገጠበት፤ አመልካች ከመነሻውም በዚህ አግባብ ክርክር አቅርበው ክርክራቸውን የሚያስረዳ ማስረጃ በማስረጃ ዝርዝራቸው ላይ አመልክተው አለመቅረባቸው አመልካች በውርስ ሀብት የኪራይ ድርሻዬ ስጠቀም የቆየሁ በመሆኑ የይርጋው አቆጣጠር ሊቋረጥ ይገባል በማለት ያቀረቡት ክርክር በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡትን ክርክር መሰረት ያላደረገ መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ፤ይህም የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካች የወራሽነት መብት በፍ/ብ/ህ/ቁ.1000(1) መሰረት በሶስት አመት ይርጋ የታገደ ነው በማለት የደረሱበት መደምደሚያ የአመልካችን የስር ፍርድ ቤት ክርክር፤ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን አስገዳጅ የህግ ትርጉሞችና ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት መሆኑን ስለሚያሳይ ተከታዩን ወስነናል፡፡

# <u>ውሳኔ</u>

1.የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.181775 ሚያዚያ 30 ቀን 2015 ዓም የሰጠው ፍርድና ይህንን ፍርድ በማፅናት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.310989 ጥቅምት 08 ቀን 2016 ዓም የሰጠው ብይን በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስነስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9(1)(ለ) መሰረት ፀንቷል፡፡

2.ግራ ቀኙ በሰበር ክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

<u>ጉዳዩ ውሳኔ ስላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡</u>

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁጥር 258571
ጥር 29 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ገበየሁ ፈለቀ

ደረጀ አያና

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

ብርሃኑ መንግሥቱ

**አመልካች፡-ደጀኔ ቶሎሳ ፡-የቀረበ የለም።**
**ተጠሪ፡- የኦሮሚያ ጠቅላይ አቃቤ ህግ፡-ደሳለኝ ሞሲሳ፡-ቀረቡ።**

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ የፍርድ ተሰጥቷል።

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ጥር 24 ቀን 2016 ዓ.ም ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ አመልካች የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 31(2) በመተላለፍ የእምነት ማጉደል ወንጀል ፈጽሟል በሚል በስር የምዕራብ ሸዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠውን ውሳኔ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 437074 ታህሳስ 02 ቀን 2016 ዓ.ም የቅጣት ውሳኔውን በማሻሻል በመወሰኑ ውሳኔው መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በሚል ነው።

ክርክሩ የተጀመረው በምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረበው ክስ በአጭሩ አመልካች የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 31(2) ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ የማይገባውን ጥቅም ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ በምዕራብ ሸዋ ዞን ጮቢ ወረዳ የጮቢ ሲርባ ክላስተር ሁለገብ የገበሬዎች ህብረት ስራ ማህበር መጋዘን ሰራተኛ ሆኖ ከጥር 1 ቀን 2011 ዓ.ም

ጀምሮ ተቀጥሮ ሲሰራ በነበረበት ጊዜ ከጥር 01 ቀን 2011 ዓ.ም እስከ ጥር 25 ቀን 2014 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በተደረገው ኦዲት በጠቅላላው ብር 3,235,839.28 (ሶስት ሚሊየን ሁለት መቶ ሰላሳ አምስት ሺህ ስምንት መቶ ስላሳ ዘጠኝ ብር ከ28/100) የመንግስት እና የህዝብ ንብረት በማጉደል ለግል ጥቅሙ በማዋሉ በከፍተኛ እምነት ማጉደል ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡አመልካችም የተከሰበትን ወንጀል ክደው የተከራከሩ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የቀረበውን ማስረጃ እንደዚሁም የቀረበው ጉዳይ ተጨማሪ ኦዲት እንዲደረግ በማድረግ አመልካች በ2013 ዓ.ም ከቀረበውን የምርት ማሳደጊያ ግብዓት ብር 203,022.81(ሁለት መቶ ሶስት ሺህ ሀያ ሁለት ብር ከ81/100) የሚያወጣውን ማጉደሉ በኦዲት ውጤት የተረጋገጠ መሆኑንና በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 31(2) ስር ጥፋተኛ መሆኑን በመጥቀስ አመልካች ከዚህ የወንጀል ድርጊት ያገኘውን ጥቅም ወይም በዚህ የሙስና ወንጀል ድርጊት የደረሰውን ጉዳት ግምት ውስጥ በማስገባት የወንጀሉ ቅጣት ደረጃ ከፍተኛ ነው በማለት በ11 (አስራ አንድ) ዓመት ጽኑ እስራት እና በብር 2000.00 (ሁለት ሺህ ) የገንዘብ ቅጣት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡

አመልካችም በተሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታውን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታው ተቀባይነት ባለማግኘቱ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት ለማሳረም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡የሰበር አቤቱታው የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም አመልካች ከሶስት ሚሊዮን ብር በላይ አጉድሎ መገኘቱ በኦዲት ውጤት የተረጋገጠ በመሆኑ በመንግስት ላይ ያደረሰው ጉዳት ከፍተኛ መሆኑን የሚያሳይ ነው በሚል በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 31(2) ሥር ጥፋተኛ መባሉ በአግባቡ መሆኑን በመጥቀስ የቅጣት ደረጃ ሲወጣ ከፍተኛ ደረጃ ስር በድጋሚ መያዙ አላግባብ ነው በማለት የቅጣቱን መነሻ መካከለኛ ስር በመያዝ በ7 ዓመት ከ8 ወር (ሰባት ዓመት ከስምንት ወር) ፅኑ የእስራት እንዲቀጣ ቅጣቱን በማሻሻል ወስኗል፡፡

አመልካችም ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ በአጭሩ በተጨባጭ በእጄ የጎደለዉ የማህበሩ ንብረት ብር 203,022.81(ሁለት መቶ ሶስት ሺህ ሃያ ሁለት ከሰማኒያ አንድ ሳንትም) ብቻ መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ በሙስና ወንጀሎች አዋጅ መሰረት ከፍተኛ ጥቅም ወይም ጉዳት ስር ሊወድቅ የማይችል ሆኖ እያለ የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በተከሰስኩበት አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 31(2) ስር የጥፋተኝነት ዉሳኔ መስጠቱ እንደዚሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔውን ማጽናቱ አግባብነት የለዉም፡፡ለሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 31 የተሰጠዉ ርዕስ በራሱ ከባድ እምነት ማጉደል የሚል ሲሆን ከአዋጁ አንቀጽ 31(1) ወደ አንቀጽ 31(2) የሚታለፈዉ በድንጋገዉ ስር እንደተዘረዘረዉ አፈጻጸሙ ወንጀሉን ከባድ አድርጎት ከሆነ ብቻ ስለሆነ አመልካች የፈጸምኩት ወንጀል በአዋጁ አንቀጽ 31(1) ስር እንጂ በአንቀጽ 31(2) ስር የሚያስጠይቀኝ አይደለም፡፡የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 የወጣዉ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 407 ስራ ላይ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በነበረበት ጊዜ ሲሆን ይህ የወንጀል ሕግ ድንጋጌ ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 881/2007 ስለተተካ፣የተገኘዉ ጥቅም ወይም የደረሰዉ ጉዳት ለመመዘን በቀጥታ የቅጣት አወሳሰን መመሪያዉን አንቀጽ 11(4) መጠቀም የህግ ድጋፍ የለዉም፡፡በተጨማሪም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 31(2) ስር ጥፋተኛ መባሌ ስህተት መሆኑን ገልጬ እንዲታረምልኝ የጠየኩትን ዳኝነት ዉድቅ ሲያደርግ እንደ ምክንያት የጠቀሰዉ አመልካች ከብር 3,000,000.00 (ሶስት ሚሊዮን) በላይ ማጉደሉ በኦዲት ሪፖርት ተረጋግጧል በማለት ቢሆንም በስር ፍርድ ቤቶች በአመልካች እጅ ጎደለ ተብሎ በኦዲት ሪፖርት የተረጋገጠዉ ብር 203,022.81(ሁለት መቶ ሶስት ሺህ ሃያ  ሁለት ብር ከሰማኒያ አንድ ሳንቲም) ብቻ ነዉ፡፡ይህም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረብኩትን የሰበር አቤቱታ በአግባቡ ሳይመረምር አመልካች በአዋጅ 881/2007 አንቀጽ 31(2) ጥፋተኛ ማለቱን ያሳያል፡፡ይህ ማለት የኦሮሚያ ሰበር ሰሚ ችሎት በእጄ የጎደለዉ ንብረት ግምት ብር 203,022.81 ብቻ መሆኑን ቢረዳ ኖሮ ጥፋተኛ የተባልኩበትን የሕግ ድንጋጌ የሚያሻሽልበት ዕድል ሰፊ መሆኑ መገመት ይቻላል፡፡ስለዚህ በማስረጃ በተረጋገጠዉ ፍሬ ነገር ጥፋተኛ የተባልኩበትን አንቀጽ ወደ አንቀጽ 31(1) ተቀይሮ የሚያስተምረኝን ቅጣት መወሰን ሲገባው በተሳሳተ መንገድ የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡትን የጥፋተኝነት ዉሳኔ ማጽናቱ ስህተት ነው፡፡የኦሮሚያ ሰበር ሰሚ ችሎት በእጄ የጎደለዉ ንብረት ከ3,000,000.00(ሶስት ሚልዮን) በላይ መሆኑ ተረጋግጧል ብሎ በዉሳኔዉ ላይ መጥቀሱ ስህተት መሆኑንና በፍ/ብሔር ኃላፊነት በኩልም ተጽዕኖ የሚያመጣብኝ መሆኑን ዘርዝሬ እንዲስተካከልልኝ ያመለከትኩ ሲሆን ችሎቱም ስህተት መፈጠሩን አምኖ ነገር ግን የተፈጠረዉ ስህተት የሚስተካከለዉ በይግባኝ ደረጃ እንጂ ማስተካከል የሚቻል አይደለም  በማለት ያቀረብኩትን አቤቱታ ዉድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ የሚል ነው፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም አመልካች የመጋዘን ሰራተኛ ሆኖ ያጎደለው የምርት ማሳደግያ ግብዓት ብር 203,022.81(ሁለት መቶ ሶስት ሺ ሀያ ሁለት ከሰማንያ አንድ) መሆኑ በስር ፍ/ቤቶች ከመረጋገጡ አንፃር ይህ የገንዘብ መጠን አሁን ባለው ነባራዊ የኢኮኖሚ ሁኔታ እና የገንዘብ ዋጋ የተገኘው ጥቅም ከፍተኛ ነው ነው አልያም የደረሰው ጉዳት ከፍተኛ ነው በማለት አመልካችን በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 31(2) ጥፋተኛ ነው በማለት የቅጣት ውሳኔ ለማስተላለፍ በቂ ነው ሊባል የሚችል ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ ለማጣራት ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡

ተጠሪም ታህሳስ 4 ቀን 2017 ዓ.ም በሰጠው መልስ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 31(2) በመተላለፍ በከባድ እምነት ማጉደል ወንጀል ተከሶ በሥር ፍ/ቤቶች ጥፋተኛ ተብሎ የተቀጣ ሲሆን አዋጁ ካለው ልዩ ባህሪ ውስጥ አንዱ የሚቀርበው ክስ በሙሉ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ጥቅምን ወይም በደረሰው ጉዳት የሚመዘን መሆኑ ነው፡፡ይህ አዋጅ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የቅጣት መመሪያ ቁጥር 02/2006 ከወጣ በኂላ በልዩ መልክ የሙስና ወንጀልን ለመደንገግ የወጣ ነው፡፡የቅጣት መመሪያ ከአዋጅ ቁጥር 881/2007 በፊት ስለወጣ ከአዋጁ ጋር በተያያዘ ይህንን መመሪያ መጠቀም አግባብ አይደለም በማለት

አመልካች ያቀረበው ተቀባይነት የለውም፡፡ምክንያቱም ይህ የቅጣት መመሪያ በልዩ ሁኔታ የወጡ አዋጆች እራሳቸውን ችለው ከነቅጣቱ በሚደነግጉት ወንጀል ላይ ተፈፃሚነት የላቸውም የሚል አላስቀመጠም፡፡ እንዲሁም ይህ አዋጁ ከዚህ ቅጣት መመሪያ በመውጣቱ ብቻ ተፈፃሚነት የለውም ካልን በአንቀጽ 3 ስር የተጠቀሱት የመመሪያው አላማ እና ግብ ተግባራዊ እንዳይሆን የሚያደርግ ነው፡፡የቅጣት መመሪያ እና የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ በባህሪው በኮድ እና በአዋጅ የተደነገጉትን የወንጀል ሕጉችን ተግባራዊ ለማድረግ የተደነገገ ሲሆን በመደበኛው የወንጀል ሕጉችን እና በሥነ-ሥርዓት ሕጉች መካከል ያለውን ግንኙነት እንዲጣጣም በሚያደርግ መልክ እና በማይቃረን መልኩ መተርጐም ይኖርበታል፡፡በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 31(2) መሠረት ወንጀሉን የሚያከብዱ ሁኔታዎች በአማራጭ ተጠቅሰዋል፡፡እነዚህም በወንጀል ድርጊት የተገኘው ጥቅም የደረሰው ጉዳት ከፍተኛ ስለመሆኑ ወይም የተከሳሽ የሥልጣን እና የኃላፊነት ደረጃ ከፍተኛ በመሆኑ ነው የሚል ሲሆን ይህ ደግሞ በአማራጭ መልክ የታቀፈ መሆኑን ያሳያል፡፡ይህ አመልካች ሥልጣኑ ዝቅተኛ ቢሆንም በድርጊቱ በዚህ የሕብረት ሥራ ማህበር ላይ የደረሰው ጉዳት ከፍተኛ መሆኑን በመገንዘብ በአንቀጽ 31(2) ስር ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣቱ የሚነቀፍ አይደለም፡፡ አመልካች አጉድሏል የተባለው ገንዘብ ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2014 ዓ.ም የነበረው የኦዲት ሪፖርት ነው እንጂ በ2017 ዓ.ም ባለመሆኑ ያጎደለውን ገንዘብ ሕጋዊ በሆነ መንገድ በሥራ ላይ አውለውት ቢሆን ምን ያክል ጥቅም ያገኙ ነበር ከሚለው አንፃር መመዘን ይኖርበታል፡፡በተጨማሪም ገንዘብ አሁን በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ዋጋ የቅሬታ ነጥብ በማድረግ መከራከሩ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አይደለም በማለት ውሳኔው እንዲፀና ተከራክረዋል፡፡

አመልካች ታሳስ 24 ቀን 2017 ዓ.ም የመልስ መልሳቸውን አቅርበው ዝርዝሩ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና የግራ ቀኙ ክርክር በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን እኛም አቤቱታ ከቀረበበት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች እና ከማስቀረቢያ ነጥብ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡እንደመረመርነዉም አመልካች የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 31(2) በመተላለፍ በእጁ የገባውንና ብር 203,022.81 (ሁለት መቶ ሶስት ሺ ሃያ ሁለት ከሰማንያ ሳንቲም) የሚገመት ገንዘብ በማጉደል ለግል ጥቅሙ በማዋል በመንግስት እና ህዝብ ላይ ጉዳት አድርሷል የሚል ነው፡፡በአመልካች ተፈጽሟል የተባለው ድርጊት በከባድ የእምነት ማጉድል ስር የሚካተት ሆኖ የስር ፍርድ ቤቶችም የተገኘው ጥቅም ከፍተኛነት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ላይ የደረሰውን ጉዳት የገንዘብ መጠን ከፍተኛነትን ከፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 አንቀጽ 11(4)(ለ) መሠረት በማድረግ በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 31(2) የጥፋተኝነት እና ቅጣት ውሳኔ ሰጥተዋል፡፡የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በበኩሉ በኦዲት የተገኘውን የገንዘብ መጠን ከግምት ውስጥ ባለማስገባት አመልካች ያገኘው ጥቅም ወይም ያደረሰው ጉዳት ከብር ሶስት ሚሊዮን በላይ ነው በሚል በድንጋጌው ሥር

የተሰጠውን የጥፋተኝነት ውሳኔ በማጽናት ቅጣቱን በማሻሻል የሰባት ዓመት ከስምንት ወር ጽኑ እስራት የቅጣት ውሳኔ የሰጠ ስለመሆኑ መገንዘብ የሚቻል ነው፡፡አመልካችም የሚከራከሩት አስቀድሞ በቀረበው ክስ ላይ በህጉ አግባብ የጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጠው በኦዲት የተረጋገጠውና አመልካች ያገኘው ጥቅም ወይም ያደረሰውን ጉዳት ከግምት ውስጥ ሳይገባ ቅጣትን ለመወሰን ሲባል በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ስር የተደነገገውን የገንዘብ መጠን እንደመስፈርት በመውሰድ አመልካች ያገኘው ጥቅም ወይም ጉዳት ከፍተኛ ነው በሚል እንደወንጀል ማቋቋሚያ መስፈርትነት ተወስዶ በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 31(2) ስር የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

አመልካች በሚሰራበት የህብረት ሥራ ማህበር በዝቅተኛ የኃላፊነት ደረጃ ላይ የሚገኝ ሆኖ የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 31 ስር የተደነገገውን በመተላለፍ በስራ አጋጣሚ በእጁ በገባው የህብረት ሥራ ማህበር በሆነው ንብረት ላይ ከባድ የእምነት ማጉደል ወንጀል የፈጸመ ስለመሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ሆኖም አመልካች በህብረት ሥራ ማህበሩ ንብረት ላይ እምነት በማጉደል ለግል ጥቅሙ አውሏል ወይም ጉዳት አድርሷል በሚል በስር ፍርድ ቤት በኦዲት የተረጋገጠው የገንዘብ መጠን ወይም የተገኘው ጥቅም ወይም የደረሰው ጉዳት ከፍተኛ መሆን አለመሆኑ ከአዋጁ አንቀጽ 31(2) ማቋቋሚያ ግዙፋዊ ፍሬ ነገር አንፃር እንዲሁም ወንጀሉ ሲፈጸም የነበረውን ነባራዊ የኢኮኖሚ ሁኔታ እና የኢትዮጵያ ብር የነበረውን የመግዛት አቅም ባገናዘበ አኳሃን ታይቶ አመልካች ጥፋተኛ ተብሎ ሊቀጣ የሚገባው በአዋጁ አንቀጽ 31(1) መሠረት ነው ወይስ አንቀጽ 31(2) መሠረት ሊሆን ይገባል የሚለውም መመርመር ያስፈልጋል፡፡

የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ሆኖ ወንጀሉ የተሰራው በመንግስት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት ወይም አደራ በተሰጠው ዋጋ ያለው ነገር ወይም ጥሬ ገንዘብ ላይ እንደሆነ በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 መሰረት ከባድ እምነት ማጉደል በመሆኑ በሙስና ወንጀል ተጠያቂ እንደሚሆንና በተጠቀሰው አኳኋን ወንጀሉ ተፈፅሞ ከተገኘ ወንጀል ፈፃሚው ከሶስት ዓመት እስከ ሰባት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከብር 10,000 (አስር ሺ) እስከ 50,000 (ሃምሳ ሺ)በሚደርስ መቀጮ እንደሚቀጣ በአዋጁ አንቀጽ 31(1) ተደንግጎ የሚገኝ ነው፡፡ በሌላም በኩል በተገኘው ጥቅም ከፍተኛነት፣የጥፋተኛው ስልጣን ወይም የህላፊነት ደረጃ ወይም በመንግስት፣በህዝባዊ ድርጅት፣በህዝብ ወይም በግለሰብ ጥቅም ላይ ያደረሰው ጉዳት ከፍተኛነት በአዋጁ አንቀጽ 31(2) መሰረት ቅጣቱን የሚያከብደው ሆኖ ይህም ከሰባት አመት እስከ ሃያ አምስት አመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከብር 50,000 (ሃምሳ ሺ) እስከ ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺ) በሚደርስ መቀጮ የሚያስቀጣ ስለመሆኑ ከድንጋጌዎቹ ይዘት መረዳት የሚቻል ነው፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አመልካች ከባድ የእምነት ማጉደል ወንጀል በመፈጸም ከፍተኛ ጥቅም አግኝቷል ወይም ከፍተኛ ጉዳት አድርሷል በሚል የተከሰሱት ከሶስት ሚሊዮን ብር በላይ ጉድለት አድርሰዋል በሚል ቢሆንም በኦዲት የተረጋገጠው የገንዘብ መጠኑ ብር 203,022.81 (ሁለት መቶ ሶስት ሺ ሃያ ሁለት) ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡የስር ፍርድ ቤት የተገኘው ጥቅም ወይም ያደረሰው ጉዳት ከፍተኛ ነው በሚል ድምዳሜ ላይ ሊደርስ የቻለው የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጠ በኃላ ቅጣትን ለመወሰን የቅጣት አወሳሰንን ትክክለኛነት እና አንድ ወጥነት ለማረጋገጥ ሲባል የተደነገገውን የቅጣት አወሳሳን መመሪያ ቁጥር 2/2006 አንቀጽ 11(4)(ለ) መሠረት በማድረግ የተገኘው ጥቅም ወይም የደረሰው ጉዳት ከብር 100,000 (አንድ መቶ ሺ) በላይ በመሆኑ ከፍተኛ ጥቅም ወይም ከፍተኛ ጉዳት ደርሷል በሚል በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 31(2) ስር ጥፋተኛ ሊባል ይገባል በሚል ነው፡፡ከሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 31(2) ስር የተገኘውንም ጥቅም ወይም የደረሰው ጉዳት ከፍተኛ ነው በሚል በወንጀሉ ማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮች ውስጥ የተጠቀሰ ቢሆንም የተገኘው ጥቅም ወይም የደረሰው ጉዳት ከፍተኛ ወይም ዝቅተኛ ነው ማለት ምን ማለት እንደሆነ መመዘኛው በአዋጁ አልተመለከተም፡፡በዚህ መሠረት የከባድ እምነት ማጉደል ወንጀል ማቋቋሚያ ፍሬ ነገር የሆነው የተገኘው ጥቅም ወይም የደረሰው ጉዳት ከፍተኛነት የህጉን ዓላማና አጠቃላይ የኢኮኖሚ ሁኔታ እና የብር የመግዛት አቅም ባገናዘበ መልኩ የዚህን ችሎት ትርጉም የሚሻ ነው፡፡በመሆኑም ፍርድ ቤት የህጉ አነጋገር አሻሚ በሚሆንበት ጊዜ በወንጀል ህግ አንቀጽ 2(4) በተፈቀደዉ ልክ ህግ አውጭው በህጉ ሊያሳካ ያሰበውን ግብ በህጉ መንፈስ መሠረት በመተርጎም ክፍተቱን ማሟላት ይገባል፡፡እንዲሁም አንድ ሰዉ ሲከሰስ በተጠቀሰበት የወንጀል ሕግ ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ ተብሎ ሊቀጣ የሚችለዉ ድንጋጌዉ ላይ ወንጀሉን የሚያቋቁሙ ሕጋዊ፣ሞራላዊ እና ግዙፋዊ ፍሬ ነገሮች (አላባዎች) እና ወንጀሉን ለማክበድ የተደነገጉ ሁኔታዎች ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 38161(ቅጽ 9) ላይ የሰጠዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ያሳያል፡፡

በዚህ መሠረት የገንዘብ ዋጋ በሚመለከት የተገኘው የገንዘብ ጥቅም ወይም የደረሰው ጉዳት ከፍተኛነት ወይም ዝቅተኛነት በአንድ ጊዜ ተወስኖ የሚቆይ ሳይሆን የገንዘብ ዋጋ በአቅርቦትና ፍላጎት፣የመንግስት ፖሊሲ፣የሀገሪቱ የኦኮኖሚ እድገት እንደዚሁም ሌሎች ምክንያቶች ላይ በመመስረት ከጊዜው ጋር ተለዋዋጭነት ባህሪይ ያለውና በጊዜ ሂደት የገንዘብ መጠን የመግዛት አቅም ላይ የሚመሰረት ስለመሆኑ ግንዘቤ የሚወሰድበት ነው፡፡ፍርድ ቤትም የተገኘውን ጥቅም ወይም የደረሰውን ጉዳት በሚመለከት የገንዘቡን መጠን መሠረት በማድረግ ከፍተኛ ነው የሚል ድምዳሜ ላይ ከመድረሱ በፊት እንደ ነገሩ ሁኔታና ነባራዊውን የገንዘብ የመግዛት አቅም ከግምት ውስጥ በማስገባት የተገኘው ጥቅም ወይም የደረሰው ጉዳት ከፍተኛ መሆን አለመሆኑን እንደየጉዳዩ ዓይነት በመለየት የህጉን ክፍተት መሙላት የሚኖርበት ነው፡፡ሆኖም የስር ፍርድ ቤቶች የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 31(2) ስር የድንጋጌውን የወንጀል ማቋቋሚያ ፍሬ ነገር የሆነውን የተገኘው ጥቅም ወይም የደረሰውን የጉዳት መጠን ከፍተኛነት የሚለውን የወንጀሉን ማክበጃ ሀረግ ወይም የወንጀል

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ማቋቋሚያ ፍሬ ነገር ሊተረጎም የሚገባው በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 አንቀጽ 11(4)(ለ) ስር የተገኘው ጥቅም ወይም የደረሰው ጉዳት መሠረት በማድረግ ጥቅሙ ወይም ጉዳቱ ከብር 100,000 (አንድ መቶ ሺ) በላይ በመሆኑ በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 31(2) ስር ጥቅም የተገኘ ወይም ጉዳት የደረሰ እንደሆነ የተገኘው ጥቅም የደረሰው ጉዳት ከፍተኛ እንደሆነ ቆጠራል በሚል አመልካች በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 31(2) ስር ጥፋተኛ ሊባል ይገባል በሚል የደረሱበት ድምዳሜ ለቅጣት አወሳሰን ዓላማ በሌላ ህግ ላይ የተመለከተውን ለአዋጅ 881/2007 አንቀጽ 31(2) ግዙፋዊ ፍሬ ነገር ማሚያ አድርጎ እንደመውሰድ ስለሚቆጠር ፣ወንጀሉ በተፈጸመበት ከጥር 1 ቀን 2011 ዓ.ም እስከ ጥር 25 ቀን 2014 ዓ.ም በኢኮኖሚ ውስጥ ያለውን ዋጋ እና የቅጣት አወሳሰን መመሪያው በወጣበት በ2006 ዓ.ም ተመሳሳይ ገንዘብ የነበረው ዋጋ በአግባቡ ያላገናዘበ እንደዚሁም የአዋጁን ዓላማ እና የወንጀል ህግ አተረጓጎም መርህን ያገናዘበ ሆኖ አልተገኘም፡፡

በስር ፍርድ ቤት እንደተረጋገጠው አመልካች የገበሬዎች ሁለገብ ህብረት ስራ ማህበር መጋዘን ሰራተኛ ሆነው ከጥር 01 ቀን 2011 ዓ.ም አስከ 2014 ዓ.ም ሲሰሩ በነበሩበት ወቅት በስራ አጋጣሚ በእጁ ከገባው ልዩ ልዩ የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶች ውስጥ ብር 203,022.81 (ሁለት መቶ ሶስት ሺ ሃያ ሁለት ከሰማንያ ሳንቲም) የሚገመት ገንዘብ ለግል ጥቅሙ በማዋል በመንግስት እና ህዝብ ላይ ጉዳት በማድረስ ከባድ የእምነት ማጉደል ወንጀል የፈጸመ ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት በኦዲት የተረጋገጠ ሆኖ እያለ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በውሳኔው ይዘት ውስጥ አመልካች ከብር 3,000,000 (ሶስት ሚሊዮን) በላይ ነው በሚል አመልካች ያገኘው ጥቅም ወይም ያደረሰው ጉዳት ከፍተኛ ነው በማለት የደረሰበት ድምዳሜ ተገቢ አይደለም፡፡ይህም ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች መሠረት ሲታይ ድርጊቱ በተፈጸመበት ጊዜ ብር 203,022.81 (ሁለት መቶ ሶስት ሺህ ሃያ ሁለት ከሰማንያ አንድ ሳንቲም) የነበረው የመግዛት አቅም ከአገራችን የኦኮኖሚ እና የብር የመግዛት አቅም ከነባራዊ ሁኔታ የዳኝነት ግንዛቤ በመውሰድ ሲታይ ከፍተኛ ጥቅም ወይም ጉዳት የሚባል ባለመሆኑ አመልካች ላይ የጥፋተኝነት እና ቅጣት ውሳኔ ሊሰጥ የሚገባው በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 31(2) ሳይሆን በወ/መ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 113(2) መሠረት ድንጋጌው ተለውጦ በአዋጁ አንቀጽ 31(1) ስር ጥፋተኛ ሊሆን ይገባል ብለናል፡፡

አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 31(1) ደረጃ ያልወጣለት በመሆኑ የወንጀሉን አፈፃፀም ሁኔታ፣የተገኘውን ጥቅም ወይም የደረሰውን ጉዳት መነሻ በማድረግ ወንጀሉን በመካከለኛ ደረጃ ስር ተመድቧል፡፡ድንጋጌውም ከሶስት ዓመት እስከ ሰባት ዓመት የሚያስቀጣ በመሆኑ አራት ዓመት እንደ መነሻ ቅጣት ተወስዶ በቅጣት እርከኖች ሰንጠረዥ ስር በእርከን 18 ስር የሚወድቅ ነው፡፡በስር ፍርድ ቤት ሦስት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች የተያዙለት በመሆኑ በቅጣት እርከን 15 ላይ የሚያርፍ ነው፡፡ይህም ከሁለት ዓመት ከሶስት ወር እስከ ሶስት ዓመት ከሶስት ወር የሚያስቀጣ በመሆኑ

አመልካች በእርከን 15 ስር ሊቀጡ የሚገባዉ ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 88(2) አንፃር የአመልካችን ግላዊ የአደገኛነት መጠን፣ያለፈ የህይወት ታሪኩን እና የኑሮውን ሁኔታ መሠረት በማድረግ የሶስት ዓመት ጽኑ እስራት እንደዚሁም የገንዘብ መቀጮን በተመለከተ አመልካች ዝቅተኛ ገቢ ያለው ስለመሆኑ በመረጋገጡ በወንጀል ህግ አንቀጽ 92(2) መሠረት የብር 2,000 (ሁለት ሺ) የገንዘብ ቅጣት ተወስኗል፡፡

ሲጠቃለል የስር ክልል ፍርድ ቤቶች በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 31(2) ስር በእምነት ማጉደል ወንጀል የተገኘውን ጥቅም ወይም የደረሰውን ጉዳት ከፍተኛነት በሚል የተገለጸውን የወንጀል ማክበጃ ግዙፋዊ ፍሬ ነገር ለቅጣት አወሳሰን ዓላማ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 ላይ የተመለከተውን መሠረት በማድረግ ሊተረጎም አይገባም፡፡ይልቁንም ይህ የድንጋገው ግዙፋዊ ነገር ሊተረጎም የሚገባው የኢኮኖሚ ዕድገት ሁኔታ አመላካቾችን እና የብር የመግዛት አቅም፣ህጉ ሊያሳካ ያሰበውን ዓላማ፣የወንጀል ህግ አጠቃላይ ዓላማና ግብ፣እንዲሁም የወንጀል ህግ አተረጓጎም መርህ መሠረት ባደረገ እኳኃን የተገኘው ጥቅም ወይም የደረሰው ጉዳት መጠን ከግምት እየገባ ተፈጻሚ ሊደረግ ይገባል፡፡በመሆኑም የክልሉ ፍርድ ቤቶች በዚህ አግባብ ለህጉ ትርጉም መስጠት ሲገባቸው የቅጣት አዋሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 ስር ከተደነገገው አንፃር የተገኘው ጥቅም ወይም የደረሰው ጉዳት ከፍተኛ ነው በማለት በአመልካች ላይ በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 31(2) ስር የሰጡት የጥፋተኝነት እና ቅጣት ውሳኔ አግባብነት በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4)(ሸ) እና 10(1)(ሐ) መሠረት መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 437074 ታህሳስ 02 ቀን 2016 ዓ.ም የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ በመ/ቁ 355880 ጥቅምት 20 ቀን 2016 ዓ.ም የሰጠውንና በምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 42798 ነሐሴ 23 ቀን 2015 ዓ.ም የተሰጠውን የጥፋተኝነት እና ቅጣት ውሳኔ በማሻሻል የሰጠው ውሳኔ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1)(ለ) መሰረት ተሻሽለዋል፡፡

2. በአመልካች ላይ የተሰጠው የሰባት ዓመት ከስምንት ወር ጽኑ እስራት ተሻሽሎ በሶስት ዓመት ጽኑ እስራት እና በብር 2,000 (ሁለት ሺህ) የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ተወስኗል፡፡
3. የምዕራብ ሸዋ ዞን ማረሚያ ቤት በአመልካች ላይ ተሻሽሎ የተወሰነውን የሶስት ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት እንዲያስፈጽም ታዟል፡፡ይጻፍ፡፡
4. የገንዘብ መቀጮው ያልተፈጸመ ከሆነ የምዕራብ ሸዋ ዞን አቃቤ ህግ ተከታትሎ እንዲያስፈጽም ብለናል፡፡ መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፣ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 260594

ጥር 30 ቀን 2017ዓ/ም

ዳኞች፡ ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ብርቅነሽ እሱባለው

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች፡ ወ/ሮ በላይነሽ ኩምሳ ቀረቡ

ተጠሪ፡ ግብርና ሚኒስቴር ነ/ፈጅ ኤልሳቤጥ መርሻ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ የቀረበው አመልካች የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 256524 በ18/6/2016ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ ቅር በመሰኘት በ27/6/2016ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ተጠሪ ለአመልካች በቁጥር ማዕ/ሠ831በ/1/2 በ4/11/2015ዓ.ም በተጻፈ በቁጥር ማዕ/ሠ831በ/1/1 በ9/10/2015 በተጻፈ የምደባ ደብዳቤ ላይ የጥጥ ልማት መሪ ስራ አስፈጻሚ ውስጥ በደረጃ XVIII በመደብ ማስታወቂያ ቁጥር 13/ግብ-1094 የስራ መደብ መጠሪያ የጥጥ ልማት መሪ ስራ አስፈጻሚ ሆነው መመደባቸውን በመግለጽ ሆኖም የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለሰራተኞች ምደባ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ከአመልካች ጋር የተወዳደሩት ተወዳዳሪው የትምህርት ደረጃ በዲፕሎማ የእንስሳት እርባታ (Animal Production and Rangeland management) ይዘው የልማት ጣቢያ ሰራተኛ ሆነው የሰሩት የስራ ልምድ አያያዝ ትክክል አይደለም በማለት ባቀረቡት ቅሬታ ላይ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው ቅሬታው ተገቢ መሆኑን ተገንዝቦ ምደባው እንዲስተካከል በወሰኑት ውሳኔ መሰረት አመልካች የጥጥ ልማት መሪ ስራ አስፈጻሚ

ሆነው የተመደቡበት የስራ ምደባ ከሀምሌ 1 ቀን 2015ዓ.ም ጀምሮ ተነስቷል በማለት በጻፈው ደብዳቤ ያሳለፈውን ውሳኔ አመልካች በመቃወም ለየኢፌዴሪ የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አስተዳደር ፍርድቤት ባቀረቡት ይግባኝ ያለኝ ዲፕሎማ እንስሳት እርባታ (Animal Production and RangeLand Management) ቢሆንም የተቀጠርኩት እና ለ6 አመት ያገለገልኩት ግን ሁሉንም የግብርና ሙያ ድጋፍ ማድረግ የሚችል አጠቃላይ እርሻ ዲፕሎማ ሙያ በሚጠይቀው ማለትም 2ኛ እና 1ኛ ደረጃ ሁለገብ ልማት ጣቢያ ሰራተኛ እንደቅደም ተከተሉ ነው፡፡ ይህ መሆኑ እየታወቀ የተቋሙ ቅሬታ ሰሚ ዲፕሎማ በእንስሳት እርባታ ይዘው የልማት ጣቢያ ሰራተኛ ሆነው የሰሩት የስራ ልምድ አያያዝ ትክክል አይደለም በሚል የተሳሳተ መረጃ የወሰነው ውሳኔ መብቴን ያሳጣኝ መሆኑ፤ በመንግስት ሰራተኝነት ካገለገልኩበት 26 አመት ለ10 ወራት ውስጥ በዲፕሎማ እንስሳት እርባታ ሙያ የእንስሳት መኖ ልማት ኤክስፐርት ከመጋቢት 1 ቀን 1995ዓ.ም እስከ ሚያዝያ 30 ቀን 1995ዓ.ም ለ 1 ወር ከ25 ቀን ብቻ መሆኑ በቀረበው የስራ ልምድ ላይ ተጽፎ እያለ ለ6 አመት በወቅቱ በቀበሌ ደረጃ 1 ባለሙያ ብቻ ተቀጥሮ በሚሰራበት ግዜ በአጠቃላይ እርሻ ሙያ በሁሉም የግብርናና ገጠር ልማት ዘርፍ ለአርሶአደሩ ሳገለግል የቆየሁበት የስራ ልምድ ተገቢነት የለውም መባሉ ሞራሌን የነካ መሆኑ፤ የተወዳደርኩት ለአመራርነት የስራ መደብ ሆኖ ሳለ በአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን የዞኑ ሴቶች ህጻናትና ወጣቶች ጉዳይ መምሪያ ኃላፊ በመሆን ከጥቅምት 1 ቀን 2003ዓ.ም እስከ መስከረም 30 ቀን 2008ዓ.ም ለ5 አመት ያገለገልኩበትን እና ከሰኔ 1 ቀን 1996ዓ.ም እስከ ታህሳስ 30 ቀን 1997ዓ.ም ለ6 ወራት በአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን በምንጃር ሸንኮራ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት የአደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ዴስክ ኃላፊ በድምሩ 5 አመት ከ6 ወር በአመራርነት ያለኝ የስራ ልምድ ያልተያዘልኝ መሆኑ፤ የሰራተኛ ድልድል ኮሚቴ በመጀመሪያ በግብርና ሚኒስቴር ማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ባሳወቀው የውድድር ውጤት መሰረት ከአመልካች ጋር የተወዳደረው ተወዳዳሪ በነጥብ በልጦኝ ተመድቦ የነበረ ሲሆን ሆኖም ተወዳዳሪዩ የበለጠኝ 11 አመት ተገቢነት ያለው 5 አመት ከ7 ወር ተገቢነት የሌለው በድምሩ 16 አመት ከ7 ወር ስለሆነ በመመሪያ ቁጥር 859 መሰረት 7.5 ነጥብ ማግኘት ሲገባው 15 ነጥብ መስጠቱ ተገቢ አይደለም በሚል ለተቋሙ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ባቀረብኩት ቅሬታ መሰረት የምደባ ደብዳቤ ከመጻፉ በፊት ቅሬታው ትክክል መሆኑ ታምኖበት ውድድሩ እንደገና የተሰራ ሲሆን በሁለተኛው የውድድር ወቅት ለተወዳዳሪዩ በመጀመሪያው ተገቢነት የለውም የተባለው ስራ ልምድ ተጨምሮ አለአግባብ 10 ነጥብ ቢሰጠውም የአመልካች ነጥብ በመብለጡ የደልዳይ ኮሚቴ ስህተተቱን አርሞ ለሁለተኛ ግዜ ማስተካከያ በማለት በማስታወቂያ ሰሌዳው ላይ የውድድሩን ውጤት አሳውቋል፡፡ በነዚህ እና ከነዚህ በፊት በነበሩ ሂደቶች በአጠቃላይ እርሻ ሙያ በሁለገብ ልማት ጣቢያ ሰራተኝነት ያገለገልኩበት የስራ ልምድ ተገቢነት ጥያቄ ሳይነሳ እንዲሁም የተቋሙ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የመጀመሪያውን የውድድር ውጤት ሲለጥፍ ላቀረብኩት ቅሬታ በቀጥታ ለኔ መልስ ሳይሰጥ ወደ ደልዳይ ኮሚቴ በመመለስ ምደባው እንደገና እንዲሰራ እና ተወዳዳሪዩ በአዲስ ቅሬታ እንዲያቀርብ መደረጉና ከሲቪል ሰርቪስ ግልጽ ባልሆነ ጥያቄ ደብዳቤ እንዲያመጣ መደረጉ የምደባውን ፍትሃዊነት እንድጠራጠር አድርጎኛል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ስለሆነም ሁለገብ ልማት ጣቢያ ሰራተኛ ሆኜ ለአርሶአደሩ በሁሉም የግብርናና ገጠር ልማት ዘርፍ ላይ የሰራሁት የስራ ልምድ ተገቢነት ያለው በመሆኑ ተይዞልኝ የመደብ መታወቂያ ቁጥር 13/ግብ-1094 በጥጥ ልማት መሪ ስራ አስፈጻሚ ደረጃ XVIII ስራ መደብ ላይ ፍርድቤቱ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴውን ሀሳብ በመሻር በሰራተኛ ደልዳይ ኮሚቴ ከሰኔ 1 ቀን 2015ዓ.ም ጀምሮ እንድሰራ የተመደብኩበትን የስራ መደብ በማጽናት እንዲወስንልኝ የሚል ነው፡፡

ተጠሪ ባቀረበው መልስ በፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች መዋቅራዊ አደረጃጀት ለውጥ መሰረት በመንግስት ሰራተኞች ድልድል አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 859/2014 አንቀጽ 6(19) እንደተደነገገው አንድ ሰራተኛ ቀድሞ ያለው የስራ ልምድ ለሚወዳደርበት የስራ መደብ ባለው ቅርበት መጠን አግባብ ያለው ወይም ተዛማጅነት ያለው መሆኑ እየተመዘነ ለድልድል እንደሚያዝ በደነገገው መሰረት የተፈጸመ ድልድል ነው፡፡ በመመሪያው መሰረት ወደ ውድድር ከመግባቱ በፊት የስራ መደቡ የሚጠይቀውን የትምህርት ዝግጅትና የስራ ልምድ በጥናት ላይ ተመስርቶ በዝርዝር የተመዘገቡና በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የጸደቀ በመሆኑ፤ ድልድሉ የሚፈጸመው በዚሁ በጸደቀ መስፈርት መሰረት የተወዳዳሪዎችን የትምህርት ዝግጅት እና ያላቸውን አገልግሎት ተዘማጅነት በማገናዘብ የተከናወነ መሆኑን፤ ከመመሪያው አንጻር አመልካች እንዲያዝላቸው ካቀረቡት የስራ ልምድ የትምህርት ዝግጅታቸው ያለውን ተግባቦት በተመለከተ አመልካች ያላቸው ዲፕሎማ እንስሳት እርባታ (Animal Production and RangeLand Management) ሆኖ ሳለ የተቀጠሩት እና ለ6 አመት አገለገልኩ ብለው ያቀረቡት የስራ ልምድ የሁለገብ ልማት ጣቢያ ሰራተኛ ስራ ሰርቻለሁ በማለት ያያዙት ማስረጃ ቢሆንም ባለው የወቅቱ የልማት ጣቢያ ሰራተኛ አደረጃጀት ከትምህርት ዝግጅታቸው ጋር ተዛማጅ በሆነው የእንስሳት ልማት ዘርፍ እንዲያገለግሉ ከሚደረግ በቀር ባልተማሩበት ሙያ ሁለገብ የልማት ጣቢያ ሰራተኛ መደብ ላይ ይመደባሉ ተብሎ ልምዱ ሊወሰድ አይገባም፡፡ ምክንያቱም በወቅቱ በነበረው አደረጃጀት የሚኖረው የልማት ጣቢያ ሰራተኛ በተፈጥሮ ሀብት ልማት ወይም በሰብል ልማት ወይም በእንስሳት ልማት ዘርፍ የትምህርት ዝግጅት አንጻር ብቻ መሆኑን በማጣራት የተሰጠ ውሳኔ ነው፡፡

በተጨማሪም የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የስራ ዝርዝር መግለጫ ቅጽ ገጽ 11 ላይ እንደተገለጸው ስራውን ለመስራት የሚያስፈልገውን የትምህርት እና ስራውን ለመጀመር የሚያስፈልግ የስራ ልምድ የሚለው ዝርዝር ላይ ለስራው የሚያስፈልገውን የትምህርት ዝግጅትን በተመለከተ የእንስሳት እርባታ ዲፕሎማ የሚል በዝርዝሩ ውስጥ ባለመኖሩ በዚህ የትምህርት ዝግጅት የተገኘ የስራ ልምድ አግባብነት የለውም፡፡ እንዲሁም አመልካች ሰርቻለሁ በማለት ያቀረቡት ሁለገብ የልማት ጣቢያ ሰራተኛ የሚል የስራ ልምድ ከላይ በተገለጸው ቅጽ የስራ ልምድ ዝርዝር ውስጥ ካለመኖሩም በላይ የስራ ልምዱ በትምህርት ማስረጃው ያልተደገፈ በመሆኑ ቅሬታቸው ተቀባይነት የለውም፡፡ አመልካች በአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን የዞኑ ሴቶችና ሕጻናት ወጣቶች ጉዳይ መምሪያ ሃላፊ በመሆን የሰራሁበት እና በአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን

በምንጃር ሸንኮራ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት የአደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ዴስክ ሀላፊ በመሆን በአመራርነት የሰራሁበት የስራ ልምድ አልተያዘልኝም በማለት ያቀረቡትን ቅሬታ በተመለከተ ከላይ በተገለጸው የስራ ዝርዝር መግለጫ ቅጽ ገጽ 11 ላይ ልምዱ የሚገኝበት የስራ አይነት አመልካች ካላቸው የስራ ልምድ ጋር ያለውን አግባብነት ወይም በዝርዝሩ የተካተተ ነው ወይም አይደለም? የሚለውን ጥያቄ የሚያስነሳ ሲሆን ተጠሪም ከዚህ አንጻር የስራ ልምዱ በዝርዝሩ ውስጥ አለመካተቱን በመመልከት አግባብ ያልሆነ የስራ ልምድ ነው በማለት ቅሬታቸውን ውድቅ አድርገናል፡፡

የአመልካች ተወዳዳሪ የሆኑት አቶ ሳምሶን አሰፋ የትምህርት እና የስራ ልምድ ማስረጃን የያዘው ፕሮፋይል እንደሚያሳየው ግለሰቡ ያቀረቡት የስራ ልምድ ለሚወዳደሩበት የጥጥ ልማት መሪ ስራ አስፈጻሚ የስራ መደብ አግባብነት እና ተዛማጅነት ያለው ሆኖ ሳለ አመልካች 5 አመት ከ7 ወር ተገቢነት የሌለው የስራ ልምድ ነው የተያዘላቸው ማለታቸው ስህተት ነው፡፡ ስለሆነም የይግባኝ ቅሬታቸው ውድቅ እንዲደረግ በማለት ተከራክሯል፡፡

የአስተዳደር ፍርድቤቱም ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምሮ በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የአደረጃጀትና ስራ ምዘና መሪ ስራ አስፈጻሚ የአመልካችም ሆነ ስራ መደቡ ላይ የተመደበው ሰራተኛ አቶ ሳምሶን አሰፋ ያላቸው የስራ ልምድ ለጥጥ ልማት መሪ ስራ አስፈጻሚ ደረጃ XVIII ስራ መደብ ያለውን አግባብነት በሚመለከት በጽሁፍ ሙያዊ ማብራሪያ እንዲያቀርብ ትእዛዝ ሰጥቶ ስራ አስፈጻሚውም በ21/2/2016ዓ.ም በተጻፈ ያቀረበው ሙያዊ ማብራሪያ አመልካች ያላቸው የስራ ልምድ ስራ መደቡ የሚጠይቀውን አግባብነት ያለውን የስራ ልምድ የማያሟሉ መሆኑን በተቃራኒው በስራ መደቡ ላይ የተመደበው ሰራተኛ አቶ ሳምሶን አሰፋ ያላቸው የስራ ልምድ ስራ መደቡ የሚጠይቀውን አግባብነት ያለውን የስራ ልምድ የሚያሟሉ መሆኑን ያስረዳል፡፡ የፌደራል መንግስት ሰራተኞች ድልድል አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 859/2014 አንቀጽ 6(19) አንድ ሰራተኛ ቀድሞ ያለው የስራ ልምድ ለሚወዳደርበት የስራ መደብ ባለው ቅርበት መጠን አግባብ ያለው ወይም ተዛማጅነት ያለው መሆኑ እየተመዘነ ለድልድል እንደሚያዝ ያስገነዝባል፡፡ የዚሁ መመሪያ አንቀጽ 9(1) የድልድል ቅድመ ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ ሰራተኛው ለሚወዳደርበት ክፍት የስራ መደብ የተቀመጠውን የተፈላጊ ችሎታዎች ያሟላ መሆን እንዳለበት ደንግጓል፡፡ አመልካች የጥጥ ልማት መሪ ስራ አስፈጻሚ ደረጃ XVIII ስራ መደብ የሚጠይቀውን አግባብነት ያለውን የስራ ልምድ የማያሟሉ መሆኑ እና በስራ መደቡ ላይ የተመደበው ሰራተኛ ስራ መደቡ የሚጠይቀውን አግባብነት ያለው የስራ ልምድ የሚያሟሉ መሆኑን ከሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ከቀረበው ማብራሪያ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ በቁጥር ማዕ/ሠ831በ/1/2 በ4/11/2015ዓ.ም ያስተላለፈው ውሳኔ ጸንቷል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ከላይ በተገለጸው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት አቅርበው ፍርድቤቱም የይግባኝ ቅሬታውን መርምሮ አመልካች የጥጥ ልማት መሪ ስራ አስፈጻሚ በመሆን ከተመደቡ በኋላ እንዲነሱ የተደረገው የስራ ልምድ አያያዝ ተገቢ አይደለም በሚል ቢሆንም አመልካች ለቦታው

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

የሚያስፈልገውን የስራ ልምድ ማሟላታቸውን የውጤት ዝርዝር የተሞላበት ሰነድ ያሳያል፡፡ ሆኖም በቦታው ላይ ሊመደቡ ይገባል የተባሉት አቶ ሳምሶን አሰፋ በውድድር ወቅት ያገኙትን ውጤት እና አመልካች ያገኙትን ውጤት ከአስተዳደር ፍርድቤት መዝገብ ግልባጭ እንደተመለከትነው አመልካች በነጥብ የተበለጡት በስራ ልምድ ሳይሆን በስራ አፈጻጸም ምዘና በተሰጠ ነጥብ ነው፡፡ በዚህ ነጥብ ላይ አቶ ሳምሶን አሰፋ 8.148 የተሰጣቸው ሲሆን አመልካች ተሿሚ ተብለው ውጤት አልተሰጣቸውም፡፡ በዚህም ምክንያት አመልካች አጠቃላይ ውጤት 77.765 በማግኘት አቶ ሳምሶን አሰፋ ደግሞ 81.548 በማግኘታቸው አመልካች ለመመደብ በጠየቁበት የስራ መደብ ሳይመደቡ አቶ ሳምሶን አሰፋ ተመድበዋል፡፡

ስለሆነም አመልካች መመደብ የሚፈልጉበት ቦታ የሚያስፈልገውን የስራ ልምድ አሟልተው እያለ የስር አስተዳደር ፍርድቤት ከስራ ልምድ አያያዝ ጋር በተያያዘ አመልካች ለመመደብ የሚጠይቁት የስራ መደብ አይገባቸውም የሚል ድምዳሜ ላይ መድረሱ ስህተት ቢሆንም ከውጤት አንጻር የአቶ ሳምሶን አሰፋ አጠቃላይ ውጤት ከአመልካች የሚበልጥ በመሆኑ አመልካች በጥጥ ልማት መሪ ስራ አስፈጻሚ መደብ ላይ ሊመደቡ አይገባም በመባሉ የተፈጸመ የህግ ስህተት የለም በማለት በሰጠው ትእዛዝ ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ከላይ የተገለጹትን ውሳኔ እና ትእዛዝ በመቃወም ሲሆን ይዘቱም በፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች መዋቅራዊ አደረጃጀት ለውጥ መሰረት የመንግስት ሰራተኞች የድልድል አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 859/2014 አንቀጽ 6(19) አንድ ሰራተኛ ቀድሞ ያለው የስራ ልምድ ለሚወዳደርበት የስራ መደብ ባለው ቅርበት መጠን አግባብ ያለው ወይም ተዛማጅነት ያለው መሆኑ የሚረጋገጠው ወደ ውድድር ከመገባቱ በፊት በደልዳይ ኮሚቴ መሆን እንዳለበት የተደነገገውን በመጣስ አመልካች ባቀረብኩት ቅሬታ መሰረት አቶ ሳምሶን ተመርጦ ከነበረበት የስራ መደብ ህግና አሰራሩን ተከትሎ መነሳቱን ባለመቀበል ሀምሌ 4 ቀን 2015ዓ.ም ከውድድር በፊት ተጣርቶ ተገቢነት አለው ከተባለው 18 አመት ከአንድ ወር የስራ ልምድ ላይ የቅሬታ አጣሪ ኮሚቴ ለድልድል ኮሚቴ ትእዛዝ ቢሰጥም ለመቀነስ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ባልተሰጣቸው ስልጣን 6 አመት ከአንድ ወሩን በመቀነስ ተገቢነት ያለው የስራ ልምድ 12 አመት ብቻ በማድረግ የሚሰጠውን ነጥብ ከ17 ወደ 12 ከ20 በማውረድ የውጤት ድምሩን ከ82.765 ወደ 77.765 ዝቅ በማድረግ ከሀምሌ 1 2015ዓ.ም ጀምሮ አመልካችን በማንሳት አቶ ሳምሶንን መመደባቸው በአስተዳደር ፍርድቤቱ መዝገብ ግልባጭ ላይ ቀርቦ ሳለ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ከተመደብሽበት የስራ መደብ የተነሳሽው የስራ ልምድ ስለተቀነሰብሽ ሳይሆን የውጤት ተኮር ስላልተሞላልሽ ነው፤ አቶ ሳምሶን 8.148 ከ10 ውጤት ተኮር ሲሞላላቸው አመልካች ስላልተሞላልሽ ከውጤት አንጻር ስለተበለጥሽ ውሳኔው ትክክል ነው በማለት ይግባኙን በመሰረዝ የሰጠው ትእዛዝ የአመልካችን መብት የሚያሳጣ ነው፡፡

ስለሆነም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሲቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍርድቤት ከስራ ልምድ ጋር ተያይዞ የሰጠውን ፍርድ ስህተት ነው በማለት የሰጠው ትእዛዝ አግባብ በመሆኑ በመቀበል፤ ከውጤት ተኮር ጋር ተያይዞ የፈጸመውን የህግ ስህተት በማረም በመመሪያ ቁጥር 859/2014 መሰረት

ተደርጎ በተሰራው የሰራተኛ ድልድል ወቅት ያገኙሁት 82.765 ውጤት ተወዳዳሪዬ በዛ ግዜ ልምዱን በራሳቸውም ቢሆን አስተካክለው ከሰጡት 81.548 ውጤት ጋር ሲነጻጸር የአመልካች ውጤት በመብለጡ በቁጥር ማዕ/ሠ/8310/11 በ9/11/2015ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ከሰኔ 1 ቀን 2014ዓ.ም ጀምሮ ተመድቤ ስሰራ ከነበረው የስራ መደብ ላይ እንድመለስ ፍርድቤቱ ለተጠሪ ትእዛዝ እንዲሰጥልኝ የሚል ነው፡፡

ይህ አቤቱታቸውን ችሎቱ መርምሮ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት አመልካች ለአከራካሪው የስራ መደብ ተገቢውን የስራ ልምድ የሚያሟሉ ስለመሆኑ መረጋገጡን ጠቅሶ የስር ፍርድቤት መደቡ አይገባቸውም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ ስህተት በመሆኑ በዚህ ረገድ የሚነቀፍ መሆኑን ነገር ግን የስራ አፈጻጸም ምዘና ውጤትን መሰረት በማድረግ ይግባኙን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህቁ 337 መሰረት ሰርዣለሁ ማለቱ የድንጋጌውን ይዘትና ትክክለኛ አፈጻጸምና ቅሬታ መሰረት ያደረገ መሆን አለመሆኑን፤ እንዲሁም በጉዳዩ ላይ ከስር ጀምሮ የተሰጡት ውሳኔዎች የቀረበው ክርክር በአግባቡ ታይቶ ተገቢው ጭብጥ ተይዞና ትጋት ተደርጎበት ተጣርቶ የተወሰነ መሆን አለመሆኑን አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት በ29/2/2017ዓ.ም ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ በዚሁ መሰረት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎ ተጠሪ በ20/3/2017ዓ.ም በተጻፈ ባቀረበው መልስ የስር የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አስተዳደር ፍርድቤት እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ እና ትእዛዝ አግባብ ነው የሚልበትን ምክንያቶች በመዘርዘር የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቋል፡፡ አመልካች በ3/4/2017ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ይህ ችሎትም የአመልካችን የሰበር አቤቱታ አቤቱታ ከቀረበበት ትእዛዝ እንዲሁም ከተገቢዎቹ የህግ ድንጋጌዎች አንጻር የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸውን የመጨረሻ ውሳኔዎች ማረም ስለመሆኑ በኢፌዲሪ ህገመንግስት አንቀጽ 80(3)(ለ) እንዲሁም በፌደራል ፍርድቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4) እና 10(1) በተዘረዘሩት ድንጋጌዎች ተቀምጧል፡፡ አንድ ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻለው በፌደራል ፍርድቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4) ከ “ሀ-ሸ ” ከተዘረዘሩት ውስጥ ቢያንስ አንዱን የሚያሟላ ሆኖ በውጤቱም ፍትሕን የሚያዛባ ጉልህ የህግ ስህተት የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 2(4) ድንጋጌ ይዘት የሚያስገነዝብ ነው፡፡

በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 337 ስር በተደነገገው መሰረት ይግባኝ ሰሚ ፍርድቤት ይግባኝ ባዩን በመስማት የመጀመሪያው ደረጃ ፍርድቤት ፍርድ የሰጠበትን መዝገብ ግልባጭ መርምሮ ፍርዱ ጉድለት የለበትም ብሎ ካመነ መልስሰጪውን ሳይጠራ ይግባኙን ዘግቶ ይግባኝ ባዩን ሊያሰናብት ይችላል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

በያዝነው ጉዳይ አመልካች በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አስተዳደር ፍርድቤት ባቀረቡት ይግባኝ በጥጥ ልማት መሪ ስራ አስፈጻሚ ደረጃ XVIII የስራ መደብ በሰራተኛ ደልዳይ ኮሚቴ ከሰኔ 1 ቀን 2015ዓ.ም ጀምሮ እንድሰራ የተመደብኩበትን የስራ መደብ በማጽናት እንዲወሰንልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡ የአስተዳደር ፍርድቤቱም ተጠሪ በ4/11/2015ዓ.ም ያሳለፈውን ውሳኔ በማጽናት ለሰጠው ውሳኔ ምክንያት ያደረገው አመልካች የጥጥ ልማት መሪ ስራ አስፈጻሚ ደረጃ XVIII ስራ መደብ የሚጠይቀውን አግባብነት ያለውን የስራ ልምድ የማያሟሉ መሆኑ እና በስራ መደቡ ላይ የተመደበው ሰራተኛ የስራ መደቡ የሚጠይቀውን አግባብነት ያለው የስራ ልምድ የሚያሟሉ መሆኑን ከሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ከቀረበው ማብራሪያ ተረጋግጧል በማለት ነው፡፡ ይህን ውሳኔ በይግባኝ የተመለከተው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች ለክርክር መነሻ በሆነው የስራ መደብ ለመመደብ የሚያስፈልገውን የስራ ልምድ ያሟሉ መሆኑን የውጤት ዝርዝር የተሞላበትን ሰነድ በመመርመር አረጋግጧል፡፡ ከዚህ አንጻር ከስራ ልምድ አያያዝ ጋር በተያያዘ አመልካች ለመመደብ የሚጠይቁት የስራ መደብ አይገባቸውም የሚል ድምዳሜ ላይ የአስተዳደር ፍርድቤቱ መድረሱ ስህተት ነው በማለት ድምዳሜ ላይ የደረሰበት ጉዳይ ነው፡፡

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በአመልካች የቀረበውን ይግባኝ ሲሰርዝ ምክንያት ያደረገው በቦታው ላይ ሊመደቡ ይገባል የተባሉት አቶ ሳምሶን አሰፋ በውድድር ወቅት ያገኙትን ውጤት በመመርመር አመልካች በነጥብ የተበለጡት በስራ ልምድ ሳይሆን በስራ አፈጻጸም ምዘና በተሰጠ ነጥብ ነው፤ በዚህ ነጥብ ላይ አቶ ሳምሶን አሰፋ 8.148 የተሰጣቸው ሲሆን አመልካች ተሿሚ ተብለው ውጤት ያልተሰጣቸው በመሆኑ አመልካች አጠቃላይ ውጤት 77.765 በማግኘት አቶ ሳምሶን አሰፋ ደግሞ 81.548 በማግኘታቸው አመልካች ለመመደብ በጠየቁበት የስራ መደብ ሳይመደቡ አቶ ሳምሶን አሰፋ ተመድበዋል፡፡ ከውጤት አንጻር የአቶ ሳምሶን አሰፋ አጠቃላይ ውጤት ከአመልካች የሚበልጥ በመሆኑ አመልካች በጥጥ ልማት መሪ ስራ አስፈጻሚ መደብ ላይ ሊመደቡ አይገባም በመባሉ የተፈጸመ የህግ ስህተት የለም በሚል ነው፡፡ ሆኖም አመልካች በስር የአስተዳደር ፍርድቤት ባቀረቡት ይግባኝ ተሿሚ ነሽ ተብዬ ውጤት አለመሞላቱ አግባብ አይደለም በማለት ይግባኝ ባላቀረቡበት እና ይህን ነጥብ በተመለከተም በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ክርክር ባልተደረገበት ሁኔታ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በአስተዳደር ፍርድቤቱ በነበረ ክርክር ያልቀረበን አዲስ የክርክር ዘንግ በራሱ በማንሳት የአመልካችን ይግባኝ ለመሰረዝ ምክንያት በማድረግ ይግባኙን በመሰረዝ የሰጠው ትእዛዝ ይህ ችሎት ሊታረም የሚገባ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝቶታል፡፡ ስለሆነም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>**ውሳኔ**</u>

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 256524 በ18/6/2016ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

2. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የዘጋውን የመ.ቁ 256524 የሆነውን መዝገብ አንቀሳቅሶ አመልካች ለክርክር መነሻ በሆነው በጥጥ ልማት መሪ ስራ አስፈጻሚ ደረጃ XVIII የስራ መደብ ለመመደብ የሚያስፈልገውን የስራ ልምድ ያሟሉ መሆኑን ያረጋገጠው ፍሬጉዳይ እንደተጠበቀ ሆኖ በአመልካች በሌሎች ነጥቦች ላይ የቀረበውን የይግባኝ ቅሬታ መርምሮ ተገቢ ነው የሚለውን ውሳኔ/ትእዛዝ ሊሰጥ ይገባል በማለት ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 343(1) መሰረት መልሰንለታል፡፡
3. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍርድቤቶች ይድረሳቸው፡፡
4. መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 267231

ጥር 30 ቀን 2017 ዓ/ም

ዳኞች ፡-ገበየሁ ፈለቀ

ደረጀ አያና

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

ብርሃኑ መንግሥቱ

አመልካች ፡-ጨመሬ ቶሎሳ፡-ጠበቃ ባጫ ታዬ፡-ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- የኦሮሚያ ጠቅላይ አቃቤ ህግ፡- ግርማ ሙሉጌታ፡- ቀረቡ፡፡

ይህ መዝገብ ከሰ/መ/ቁ/ 267230 ጋር ተጣምሮ ተመርምሮ የሚከተለዉ የፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

የአሁን አመልካች በምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በ/መ/ቁ 47863 እና በመ/ቁ በመ/ቁ 47862 በሁለቱም መዝገቦች ላይ 2ኛ ተከሳሽ ሲሆን ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበው የክስ ይዘትም አመልካች የኢትዮጵያ የፌዴራል ቡና እና ሻይ ባለስልጣን ግምቢ ቅርንጫፍ የቡና ላኪ ሸኚ ስምሪት ጣቢያ ላይ ቋሚ ሰራተኛ ሆኖ በባለሙያነት ተቀጥሮ እየሰራ እያለ በቡና ንግድ ውስጥ የማጭበርበር ድርጊት በመፈጸም ለራሱ የማይገባውን ጥቅም ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ በምዕራብ ወለጋ ዞን ግምቢ ከተማ ቀበሌ 05 በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ግምቢ

ቅርንጫፍ ግቢ ውስጥ ጥቅምት 16 ቀን 2016 ዓ.ም ለማዕከላዊ ገበያ የሚቀርብ የተቀሸረ ቡና ዓይነቱ እና የሰሌዳ ቁጥሩ 3-A02958 A.A በሆነ ኤፍ.ኤስ፣አር መኪና ከነጆ ከተማ ተጭኖ በፕሎምፕ ታሽጎ የቡናው ፕሎምፕ ቁጥር GM-7 በሚባል የታሸገውን በሚልክበት ጊዜ የቡናውን መጠን አጣርቶ መላክ እያለበት የተቀሸረ 129 ኩንታል ተጭኖ እያለ 100 ኩንታል በሚል እንዲሁም ከአይራ ወረዳ በሲኖ ትራክ 210 ኩንታል ቡና የተጫነ ነዉ ተብሎ የተላከዉን ተቀብሎ በቡናው የይለፍ ወረቀት ላይ ይህንኑ መጠን በማረጋገጥ የይለፍ ወረቀት ከሰጠ በኋላ በዚሁ ቀን የተጠቀሱት መኪናዎች በጊምቢ ከተማ ልዩ ስሙ ሰርጤ ኬላ ቦታ ላይ በቁጥጥር ስር ውለዉ ሲፈተሹ 29 እና 70 ኩንታል ቡና እንደቀደም ተከተላቸዉ ከህግ ውጭ ጥራት በሌለው የማዳበሪያ ከረጢት ተጨምሮ እሱ በይለፍ ወረቀት ላይ ጽፎ ከሰጠው በላይ በተጨማሪ ተጭኖ ስለተገኘ የአዋጅ 1051/2009 አንቀጽ 19/5/ የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 433/2007 አንቀጽ 41(1)(ቀ) በመተላለፍ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት አስቦ በቡና ንግድ ውስጥ የማጭበርበር ወንጀል ድርጊት ፈጽሟል የሚል ነው፡፡

አመልካች በሁለቱም መዝገብ ቁጥሮች የቀረቡበትን ክሶች ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ክዶ የተከራከረ ሲሆን የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ሁለቱንም ክሶች ከላይ በተጠቀሱት የተለያዩ መዝገብ ቁጥሮች የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ በሁለቱም ክሶች በሰጠው ውሳኔ አመልካች በፌዴራል ቡና አንኳኋ ድርጅት ግምቢ ቅርንጫፍ ውስጥ ለማእከላዊ ገበያ የሚያልፍ ቡና መስፈርቱን አሟልቶ መጫኑን በማረጋገጥ የይለፍ ወረቀት ሰጥቶ የሚሸኝ ባለሙያ መሆኑን፤ነገር ግን በህግ የተጣለበትን ግዴታ ባለመወጣት ለስር በእያንዳነዱ መዝገብ 1ኛ ተከሳሾች ለነበሩት የኤፍ ስ አር ጭነት መኪና እና ሲኖ ትራክ ጭነት መኪና ሾፌሮች ለነበሩት ወረዳ በተሰጠው የይለፍ ወረቀት ብቻ ላይ በመመስረተ ማህተም አድርጎበት ሳያጣራ እና የቡናውን መጠን ሳያረጋግጥ መሸኘቱን፤ ይህም በአዋጅ 1051/2009 አንቀጽ 19/5/ የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 433/2007 አንቀጽ 41(1/ቀ) እና በኢትዮጵያ ቡና እና ሻይ ባለስልጣን ያወጣውን መመሪያ ቁጥር 02/2012 አንቀጽ 7.3.3.1 ስር የተጣለበትን ግዴታ ያልተወጣ መሆኑን የሚያሳይ መሆኑን፤የቡና እና ሻይ ባለስልጣን በታህሳስ 30 ቀን 2013 ዓ.ም የጻፈው ደብዳቤ የተጫነውን ቡና አትመዝኑ በማለት በግልጽ አለመከልከሉን ጠቅሶ አመልካች በተከሰሰበት በሁለቱም መዝገብ ቁጥሮች ላይ ክስ በቀረበበት አንቀጽ ስር ጥፋተኛ ነዉ በማለት በእያንዳንዱ መዝገብ በቀረበዉ ክስ በ3 ዓመት ጽኑ እስራት እና በ5000 (አምስት ሺ ህ) ብር በሁለቱም መዝገቦች ላይ በቀረበዉ ክስ በድምሩ በ6 ዓመት ጽኑ አስራት እና በብር 10000 /አስር ሸህ ብር/ የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ

እንዲቀጣ ወስኗል፡፡የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምዕራብ ቋሚ ችሎት የቀረበለትን ቅሬታ በመ.ቁጥር 47862 እና 47863 አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ጉድለት የለውም በማለት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 195(2/ለ/2) መሰረት  አጽንቷል፡፡

የአሁን ሰበር ቅሬታ የቀረበው በየደረጃው ያሉ ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት ለማስለወጥ ነው፡፡የሰበር ቅሬታውም በአጭሩ አመልካች የፌዴራል ቡና እና ሻይ ባለስልጣን ግምቢ ቅርንጫፍ ባለሙያ ሲሆን የስራ ድርሻው ከወረዳዎች ወደ ማዕከላዊ ገበያ ለመሄድ ወደ ቅርንጫፍ የሚመጣውን ቡና በመቀበል የይለፍ ወረቀት በድርጅቱ በመለጠፍ ወደ ማዕከላዊ ገበያ ማድረስ ነው፡፡በደንቡ እና መመሪያው እንዲሁም በነበረው አሰራር ከወረዳ ተጣርቶ የቀረበው ቡና መጠን እና ደረጃ ላይ በተጨማሪ በቅርንጫፍ ደረጃ የፌዴራል ቡና እና ሻይ ባለስልጣን ባለሙያ የቡና መጠን እና ጥራት ደረጃን በመለየት ሲልክ የነበረ ቢሆንም  በደብዳቤ ቁጥር ኢት/ቡ/ሻ/ባ/መ-060/497 ታህሳስ 30/2013 ከኢትዮጵያ ቡና እና ሻይ ባለስልጣን ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጅት በተጻፈ እና በደብዳቤ ቁጥር ኢት/ቡ/ሻ/መ-046/1000 ጥር 3/2013 ለኢትዮጵያ ጉሙሩክ ኮሚሽን በተጻፈ ደብዳቤ ለማዕከላዊ ገበያ ቡና ከማቅረብ ጋር ተያይዞ መጓተት ያለ መሆኑን እና በዚህ ረገድ ሪፎርም እየተሰራ ያለ መሆኑን በመግለጽ ከጥር 3 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ቡና በወረዳ ደረጃ በጥንቃቄ ተጣርቶ መጠኑ ተመዝኖ፣ጥራቱ ተለይቶ ለፌዴራል ቡና እና ሻይ ባለስልጣን የፌዴራል ቅርንጫፍ እንዲላክ የፌዴራል የቡና እና ሻይ ባለሙያ ደግሞ ሰነድ የማዘጋጀት ስራ እና የመላክ ስራ ብቻ እንዲሰራ መመሪያ ተላልፏል፡፡ ከዚህም ሌላ ከምዕራብ ወለጋ ዞን ገበያ ጽ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር WDG/4-16/9168 ጥቅምት 28 ቀን 2016 ዓ.ም የተጻፈ መግለጫ እና አቃቤ ህግ እንደ ማስረጃ ያቀረበውም የጥራት ስራ፣የደረጃ እና መጠን እና ሌሎች ነገሮችን ከማጣራት ጋር ተያይዞ ያለውን በወረዳ እና ከተማ ደረጃ የሚያልቅ መሆኑን እና የፌዴራል ቡና እና ሻይ ባለስልጣን ባለሙያ ከወረዳ ወይም ከከተማ የተሰጠውን የይለፍ ፈቃድ ወደ ድርጅቱ በመቀየር መሸኘት/መላክ ብቻ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ የፌዴራል ቡና እና ሻይ ባለስልጣን ባለሙያ እንደ ቀድሞ ከወረዳ ላይ ተጭኖ የመጣውን ቡና አውርዶ መቁጠርም ሆነ መመዘን እንዲሁም የጥራት ደረጃውን መለየት የማይችል መሆኑን እና ስራው በቀጥታ ሁሉ ነገሩ ከወረዳ ላይ ተጣርቶ የመጣውን ቡና ከወረዳ ላይ የመጣውን ሰነድ ወደ ድርጅት ሰነድ በመቀየር ፕሎምፑን ብቻ በድጋሚ በማሸግ ወደ ማዕከላዊ ገበያ የሚልክ መሆኑን ያሳያል፡፡የአሁን አመልካችም እነዚህን ደብዳቤዎች እንደ መከላከያ ማስረጃ በስር ፍርድ ቤቶች ያቀረበ ሲሆን በስር ፍርድ ቤት ቀርበው የተሰሙ የሰው የመከላከያ ምስክሮችም ከ ጥር 03 ቀን

2013 ዓ.ም ጀምሮ የኢትዮጵያ ቡና እና ሻይ ባለስልጣን ለሚመለከተው አካል በጻፈው ደብዳቤ መሰረት ለማዕከላዊ ገበያ የሚቀርብ ቡና ጥራቱም ሆነ ደረጃው እና መጠኑ በወረዳ ባለሙያ ደረጃ ተጣርቶ ወደ ኢትዮጵያ ቡና እና ሻይ ባለሥልጣን ቅርንጫፍ የሚላክ መሆኑን እና በቅርንጫፍ ደረጃ ያለው ባለሙያ ደግሞ ከወረዳ ተዘጋጅቶ የመጣውን ሰነድ ወደ ድርጅት በመቀየር ቡናውን በድጋሜ GM-7 የሚል ፒሎምፕ አድርጎበት ከመላክ ያለፈ ቡናውን ፈትቶ ማየትም ሆነ መመዘን የማይችል መሆኑን ያሳያል፡፡አሁን ክርክር ያስነሳው ቡና ከነጆ እና ከአይራ ወረዳዎች የመጣውንና በሰነዱ ላይ የተጠቀሰውን ቡና በባለሙያ የይለፍ ፈቃድ ተሰጥቶት የአሁን አመልካች እየሰራበት ባለው የፌዴራል ቡና እና ሻይ ቅርንጫፍ ሽኝት የተደረገለት ሲሆን የአሁን አመልካችም በቅርንጫፍ ደረጃ ይሄንኑ በመግለጽ ከላይ የተገለጸውን ደብዳቤ የይለፍ ፈቃድ ወደ ድርጅት በመቀየር እንዲሁም GM-7 የሚል ፒሎምፒ አድርጎበት ልኳል፡፡ይህ ደግሞ የአሁን አመልካች ከሚሰራበት ድርጅት ዋና መስሪያ ቤት እንደ መመሪያ በተጻፉ ደብዳቤዎች መሰረት እና በድርጅቱ ውስጥ በተዘረጋው አሰራር መሰረት ሰነድ በማዘጋጀት የላከ መሆኑን ነው፡፡አመልካች በድርጅቱ ውስጥ በተዘረጋው አዲስ አሰራር መሰረት የፈጸመ ከሆነ ደግሞ ወንጀል ለመፈጸም የሀሳብ ክፍል (mental element) ስለሌለው ወንጀል ፈጽሟል የሚያስብለው አይደለም፡፡የስር ፍርድ ቤቶች የአሁን አመልካች ወንጀል ለመፈጸም የሀሳብ ክፍል ሳይኖረው ወንጀል ፈጽሞዋል በማለት አዋጅ ቁጥር 1051/2009 አንቀጽ 19 (5) ስር ጥፋተኛ ማድረጋቸው እና መቅጣታቸው መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ነው፡፡ጥፋት ፈጽሟል ቢባል እንኳን በወንጀል ህግ አንቀጽ 420 ድንጋጌ ስር የስራ ግዴታን በአግባቡ ባለመወጣት ስር ሊሸፈን የሚችል በመሆኑ የተፈጸመው ስህተት ታርሞ ተገቢ ውሳኔ እንዲሰጥልኝ ሚል ነው፡፡

አመልካች በሁለቱም መዝገቦች ላይ ያቀረበው ቅሬታ በሰበር ሰሚው ችሎት ተመርምሮ በተመሳሳይ መልኩ በአመልካች ተፈጽሟል የተባለው ድርጊት የወንጀል ተጠያቂነትን የሚያስከትል ስለመሆን አለመሆኑ፤ተጠያቂነትን የሚያስከትል ነው ከተባለም የክርክር መነሻ ለሆነው ድርጊት ተፈጻሚነት ያለው የህግ ድንጋጌ የትኛው ነው የሚለውን ለማጣራት ሲባል ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡

ተጠሪም በቀረበው የሰበር አቤቱታ ላይ በሰጠው መልስ አመልካች የተከሰሰበትን ወንጀል ስለመፈጸሙ በአቃቤ ህግ ምስክር ተረጋግጦበታል፡፡አመልካች ድርጊቱን ሆን ብሎ የፈፀመ መሆኑን እና የስራ ግዴታውን እንደተወጣ አድርጎ እንደ መከላከያ ማስረጃ ቢያቀርብም በአዋጅ ቁጥር 1051/2009 አንቀጽ 19(5) መሰረት <u>በቡና ንግድ ስራ ውስጥ የማጭበርበር ስራ የሰራ ሰው</u>

ድርጊቱን የፈጸመው በቸልተኝነት እንኳን ቢሆን እንደሚያስቀጣ ይደነግጋል፡፡ስለሆነም አመልካች የተቀጣበትን የወንጀል ድርጊት በወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀጽ 23 መሰረት ወንጀል ለመመስረት መመዘኛዎችን የሚያሟላ በመሆኑ በዚህ ረገድ ያቀረበው ቅሬታ ተገቢነት ያለው አይደለም፡፡ አመልካች መከሰስ ያለብኝ በአዋጅ ቁጥር 1051/2009 ስር ሳይሆን በወ/መ/ህግ አንቀጽ 420(1) ስር መሆን አለበት በማለት ያቀረበው ቅሬታም ተገቢ አይደለም፡፡ ምክንያቱም አዋጅ ቁጥር 1051/2009 አንቀጽ 19(5) እና የወንጀል ህግ አንቀጽ 420(1) ይዘታቸውም ሆነ ሀሳባቸው የተለያየ ነው፡፡ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ ያቀረበው አመልካች ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ በቡና ግብይት ውስጥ አሳሳች ድርጊት ፈጽሟል በሚል ነው እንጂ አመልካቹ የስራ ግዴታውን በአግባቡ ሳይፈጽም በመቅረቱ ጉዳት አድርሷል በሚል በማመሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ባለመኖሩየአመልካች ቅሬታ ውድቅ እንዲደረግ በማለት ጠይቋል፡፡

አመልካችም የሰበር ቅሬታዉን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርቦ ክርክሩ ክርክሩ ተጠቃሏል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ ይዘት አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተዉን የሚመስል ሲሆን እኛም ቅሬታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ እና ከህጉ አንጻር መዝገቡን መርምረል፡፡ እንደመረመርነውም በክርክሩ እልባት ማግኘት የሚገባው ነጥብ ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረበው ክስ መሠረት የማስረዳት ግዴታውን ተወጥቷል ወይስ አልተወጣም የሚል ነጥብ መሆኑን በመገንዘብ የሰበር አቤቱታ በቀረበበት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ ሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት የህግ ድንጋጌ አዋጅ ቁጥር 1051/2009 አንቀጽ 19(5) እና የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 433/2007 አንቀጽ 41(1/ቀ) ተላልፎ በቡና ንግድ ላይ የማጭበርበር ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ ሲሆን አዋጅ ቁጥር 1051/2009 አንቀጽ 19(5) ማንኛዉም በቡና ግብይት የተሰማራ ይሁን ከቡና ግብይት ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ግንኑነት ያለዉ ሰዉ ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት አላግባብ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በቡና ጥራትም ይሁን ግብይት ላይ አሳሳች ድርጊት የፈጸመ እንደሆነ የሚል ሲሆን ደንብ ቁጥር 433/2007 አንቀጽ 41(1/ቀ) ደግሞ የቡና ግብይት ተቆጣጣሪ ተግባራት በየደረጃዉ የሚጓጓዝ የአቅርቦት፤የሀገር ዉስጥ ፍጆታ እና የዉጭ የንግድ ቡና አጣርቶ በፕሎምፕ በማሸግ መሸኘት መሆኑን የሚያሳይ ነዉ፡፡ከአዋጁም ሆነ ከደንቡ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለዉ አመልካች እያንዳንዱን ቡና የሚያጓጉዘዉን መኪና ሁሉ ጭነቱን እንዲያራግፍ አድረጎ በመኪናዉ ላይ የተጫነዉን ቡና ስንት ኩንታል እና ስንት ኪሎ እንደሆነ ቆጥሮ እና መዝኖ መሸኛ ወይም የይለፍ ወረቀት የመስጠት ኃላፊነት ያለበት መሆኑን የሚያሳይ አይደለም፡፡

በመሰረቱ አንድ ሰዉ ወንጀል ፈጸመ የሚባለዉ ወንጀልነቱ እና አስቀጪነቱ በህግ የተደነገገ ድርጊት ፈጽሞ በተገኘ ጊዜ መሆኑ እና አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለዉም ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ህጋዊ፤ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተዉ ሲገኙ ብቻ መሆኑ በወንጀል ህግ አንቀጽ 23 (1/2) ስር ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን በወንጀል ጉዳይ የሚቀርብ የክስ ማመልከቻ ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል መሰረታዊ ነገር እና ሁኔታዎች የተገለጹበት ሊሆን እንደሚገባ እና ስለወንጀሉ እና ስለሁኔታዉ የሚሰጠዉ ዝርዝር መግለጫ ተከሳሹ ፈጸመ የተባለዉን ተግባር ወንጀል ከሚያደርገዉ ህግ አነጋገር ጋር በጣም የተቀራረበ መሆን እንደሚገባዉ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 111 እና 112 ድንጋጌዎች ላይ ተደነገገዉም ከሳሹን ወገን በ/ወ/ህ/ሕ/ቁ 23(2) ስር የተመለከተዉን የወንጀል ማቋቋሚያ  ፍሬ ነገሮች ተሟልተዉ መገኘታቸዉን ለማስረዳት እንዲያስችለዉ መሆኑን ከድንጋጌዎቹ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በሌላ አነጋገር ከሳሽ ወገን በክሱ መሰረት አስረድቷል ለማለት የሚቻለዉ ቀደም ሲል በተጠቀሱት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 111 እና 112 ድንጋጌዎች መሰረት አዘጋጅቶ ባቀረበዉ የክስ ማመልከቻ መሰረት ተከሳሹ ወንጀል መፈጸሙን ማስረዳት በቻለ ጊዜ ነዉ፡፡(በሰ/መ/ቁ 91535 የተሰጠን የህግ ትርጉም ይመለከቷል) ፡፡

በያዝነዉ ጉዳይ ከላይ የተመለከተዉን የክስ ነጥቡ ለማዘስረዳት የቀረቡት የተጠሪ ምስክሮች በሰጡት ምስክርነት ሁለቱ መኪናዎች እያንዳንዳቸዉ ጭነዋል ተብሎ ማረጋገጫ ከተሰጠባቸዉ 100 ኩንታል ቡና እና 210 ኩንታል ቡና በተጨማሪ እንደቅደም ተከተላቸዉ 29 ኩንታል እና 70 ኩንታል ቡና ኬላ ላይ ሲፈተሽ በትርፍነት የተገኘ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሲሆን ማረጋገጫዉ የተሰጠዉም ጭነቱ መጀመሪያ ከተነሳበት ከነጆ ከተማ እና አይራ ወረዳ መሆኑ የተረጋገጠ ነዉ፡፡ የአመልካች የስራ ኃላፊነትም ቡናዉ ከተነሳበት ቦታ ታሽጎ የተላከ መሆኑን በማረጋገጥ  የመጣውን ሰነድ ወደ ድርጅት ሰነድ በመቀየር ፕሎምፑን ብቻ በድጋሜ በማሸግ ወደ ማዕከላዊ ገበያ መላክ መሆኑን ከማረጋገጥ ዉጭ እያንዳንዱን ቡና ጭኖ የሚመጣ መኪና እንዲራገፍ እያደረገ እና እየመዘነ በመቁጠር እና እንደገና እንዲጫን በማድረግ ብዛቱ ስንት እንደሆነ አረጋግጦ የመላክ ግዴታ ያለበት መሆኑን በማሳየት አቃቤ ህግ የማስረዳት ግዴታዉን በበቂ ሁኔታ ያልተወጣ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነዉ፡፡በመሆኑም ፍርድ ቤቱ አቃቢ ህግ አግባብ ባለው ማስረጃ   ክሱን ባላስረዳበት ሁኔታ አመልካችን በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 141 ድንጋጌ መሠረት በነፃ እንዲሰናበት መወሰን ሲገባው በክሱ በተመለከተው በድንጋጌው ስር ተከላከል ማለቱ አግባብ አይደለም፡፡

ሲጠቃለል ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ የምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካችን በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 141 ድንጋጌ መሰረት በነጻ ማሰናበት ሲገባዉ የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ ትእዛዝ መስጠቱም ሆነ በመጨረሻም የአቃቤ ህግን ማስረጃ አላስተባበለም በማለት የሰጠዉ

የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ማጽናቱ ከላይ የተመለከቱትን መሰረታዊ የወንጀል ህግ እና የወንጀል ስነ ስርዓት ህግ ድንጋጌዎችንና የአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4)(ለ)፣10(1)(ሪ) መሠረት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. አመልካችን አስመልክቶ በምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በ/መ/ቁ 47863 የካቲት 12 ቀን 2016 ዓ/ም እና በመ/ቁ 47862 የካቲት 21 2016 ዓ/ም ተሰጥቶ በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በ/መ/ቁ 429735 እና በመ/ቁ 429736 ሚያዚያ 15 ቀን 2016 ዓ/ም የጸናዉ ፍርድ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ተብሎ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 9/1(ሀ) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ ባቀረበዉ የሰዉ እና የሰነድ ማስረጃ አመልካች የወንጀል ድርጊቱን መፈጸሙን ያላስረዳ እና በህግ የተጣለበትን የማስረዳት ሸክም ያልተወጣ በመሆኑ አመልካች ከተከሰሰበት የወንጀል ክስ በነጻ እንዲሰናበት ተወስኗል፡፡
3. አመልካች በሁለቱም የምዕራብ ወለጋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወንጀል መዝገቦች ላይ ከተላለፈበት የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በነፃ የተሰናበተ በመሆኑ በሌላ ጉዳይ የማይፈለግ ከሆነ በዚህ ጉዳይ ታስሮ የሚገኝበት ማረሚያ ቤት ከእስር እንዲፈታው ታዟል፡፡ይጻፍ፡፡
4. አመልካች ተጥሎባቸዉ የነበረዉን የብር 10,000 (አስር ሺ.ህ) የገንዘብ የመቀጮ ለመንግስት ገቢ አድርገዉ ከሆነ ተመላሽ እንዲደረግላቸዉ ለሚመለከተዉ ክፍል ይጻፍ ፡፡
5. ይህ መዝገብ ከመዝገብ ቁጥር 267230 ጋር ተጣምሮ ተመርምሮ የተወሰነ ስለሆነ የዚህ ውሳኔ ቅጅ የዚያም መዝገብ አካል ይሁን ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡ የማይነበብ የአምስትዳኛ ፊርማ አለበት

<u>ማስታወሻ</u>፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

**የሰ/መ/ቁ 273594**

ጥር 29 ቀን 2017ዓ.ም

**ዳኞች ፡- ገበየሁ ፈለቀ**

**ደረጀ አያና**

**ደጀኔ አያንሳ**

**ኑሪዲን ከድር**

**ብርሃኑ መንግሥቱ**

**አመልካች፡- አቶ ዮሀንስ ካሳዬ - ጠበቃ ሄኖክ አበበ ቀረበ**

**ተጠሪ፡- የፍትህ ሚኒስቴር ዓቃቤ ሕግ - አልቀረበም**

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ፍርድ</u>**

ጉዳዩ የዋስትና መብት አተገባበር የሚመለከት ነው፡፡ክርክሩ የተጀመረው በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪ በአመልካች ላይ በመሰረተዉ ክስ አመልካች በኢፌዲሪ ወንጀል ሕግ አንቀፅ 32(1/ሀ) እና 590(1/ሀ እና 2/ሐ) ስር የተደነገገዉን በመተላለፍ በዋና ወንጀል አድራጊነት በሚፈፀም የሰው ማገት(መጥለፍ) ወንጀል በመፈጸሙ ተከሷል የሚል ነው፡፡ ይህንን ተከትሎ አመልካች የዋስትና መብቱ እንዲከበርለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡ፍርድ ቤቱም የዋስትና መብት ጥያቄውን በተመለከተ በሰጠው ትዕዛዝ አመልካች የተከሰሰበት ክስ በመርህ ደረጃ ዋስትና የማያስከለክል ቢሆንም እንጂ በክሱ ላይ የተጠቀሰውን ድርጊት አፈፃፀም በተመለከተ አመልካች የመከላከያ ሰራዊት የደንብ ልብስ ለብሰው እና የጦር መሳሪያ ይዘው ፈፀመ ተብሎ በክስ ዝርዝር ላይ ባይገለፅም ድርጊቱን ፈፅሞ ከሆነ ተሳትፎዉ ወደ ፊት ማስረጃ

በመስማት ጊዜ የሚታይ ሆኖ በአጠቃላይ ከክሱ ዝርዝር ፍርድ ቤቱ የወንጀሉ አፈፃፀሙ ከባድ ሆኖ ስለአገኘዉ አመልካች ምን አልባት ወደፊት የወንጀል ድርጊቱን መፈፀሙ ተረጋግጦ ጥፋተኛ የሚባል ከሆነ ሊጣልበት የሚችለው ቅጣት ከባድ ሊባል የሚችል በመሆኑ ይህን ፈርቶ ቀጠሮ አክብሮ ይመጣል የሚል እምነት የለንም በማለት የአመልካችን የዋስትና መብት ጥያቄ ዉድቅ አድርጓል።

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ቢሆንም ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 272030 ላይ በቀን 19/03/2017 ዓ.ም በሰጠዉ ትእዛዝ የሥር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሰርዞበታል።

አመልካች በቀን 03/04/2017 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበው ከላይ በተገለፀው አግባብ በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት ሲሆን የአቤቱታው አጭር ይዘት - አስቀድሞ በነበረው የጊዜ ቀጠሮ መዝገብ የዋስትና መብቴ ተጠብቆልኝ ጉዳዩን ውጪ ሆኜ ስከታተል የነበረ ሲሆን ከዚህም ባለፈ ክሱ በፖሊስ አማካኝነት ደርሶኝ የክሱን አይነትና የቅጣቱን ክብደት ከተረዳሁ በኋላም ቢሆን የገባሁትን የዋስትና ግዴታ በማክበር ክሱ ሊሰማ በተቀጠረበት ቀን ችሎት ቀርቤአለው።አመልካች ቋሚ የመኖሪያ አድራሻ ያለኝ ሲሆን ሌሎች ተከሳሾች የዋስትና ግዴታቸውን ሳያከብሩ ሲቀሩ እኔ ብቻዬን መቅረቤ የዋስትና ግዴታዬን አክብሬ የምቀርብ ስለመሆኑ ማሳያ ነው።ይህ በሆነበት ሁኔታ ፍርድ ቤቱ ቅጣቱ ከፍተኛ ሊሆን ስለሚችል አመልካች የዋስትና ግዴታውን አያከብርም በማለት የዋስትና ጥያቄዬን ውድቅ ያደረገበት መንገድ በምንም አይነት በቂና ሕጋዊ በሆነ ምክንያት ያልተደገፈ ግምት ነዉ። እንዲሁም የአመልካችን በሕግ ፊት ንፁህ ሆኖ የመገመት እና መሰረታዊውን ሕገ መንግስታዊ የዋስትና መብት ድንጋጌዎችን የጣሰ ከመሆኑም በተጨማሪ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አስገዳጅ ውሳኔዎች የሚቃረን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ጥሰት የተፈፀመበት በመሆኑ ታርሞ የዋስትና መብቴ ይጠበቅልኝ በማለት አመልክቷል።

ችሎቱ የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት የዋስትና መብት በመከልከል የሰጠዉ ዉሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ አንቀጽ 67 ድንጋጌ እና ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 269430 እና በሌሎች መዛግብት ላይ የሰጠዉን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የተከተለ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ አዝዟል።

ተጠሪ በቀን 25/04/2017 ዓ.ም የተጻፈ መልስ በማቅረብ - ምንም እንኳን አመልካች የተከሰሰበት የወንጀል ድንጋጌ ዋስትና የሚያስከለክል ባይሆንም የመከላከያ ሰራዊት የደንብ ልብስ በመልበስ የሕግ አካለት ነን በሚል የሚፈፀም የሰው መጥለፍ ወንጀል በተበራከተበት እና አመልካችም በዚሁ ውስጥ ተሳትፎ የወንጀል ክስ የቀረበበት በመሆኑ እና ሊወሰንም የሚችለው ቅጣት ከፍ ያለ መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት የዋስትና ጥያቄውን የሥር ፍርድ ቤት ውድቅ ማድረጉ ተገቢ ነው።ፍርድ ቤቶች ሁኔታዎችን ከግምት

ውስጥ በማስገባት ዋስትና መከልከላቸው እንደ ንፁህ የመገመት መብትን የሚጥስ ነው የሚያስብል ድምዳሜ ላይ አያስደርስም፡፡ በሰ/መ/ቁጥር 134228 ላይ በተሰጠዉ የሕግ ትርጉም አንድ ተከሳሽ የዋስትና መብት ቢከበርለት ግዴታውን አይፈፅምም ተብሎ ግምት የሚወሰደው በቂ እና ሕጋዊ ሊባሉ በሚችሉ ምክንያቶች ሊሆን እንደሚገባ እንዲሁም በቂ እና ሕጋዊ የሚባሉ ምክንያቶች ደግሞ ከተለያዩ አከባቢያዊ ሁኔታዎች አንፃር ፍርድ ቤቶች ግንዛቤ ሊወስዱበት የሚችል እንደሆነ ተወስኗል፡፡ በመሆኑም ለአመልካች የዋስትና መብት መከልከሉ አግባብ ነው፡፡እንዲሁም በሰ/መ/ቁጥር 59304 ላይ የዋስትና መብትን ለመንፈግ ተከሳሽ የተከሰሰበት የወንጀል ክሶች ብዛት እና ከባድነት መነሻ ሊሆን እንደሚችል ውሳኔ ተሰጥቶበታል፡፡ስለሆነም ከወንጀሉ አፈፃፀም ክብደት እና ድርጊቱን መከላከያ ሰራዊት የደንብ ልብስ ከለበሱ ፖሊስ ነን ከሚሉ ግለሰቦች ጋር በመሆን ከፈፀመ በኋላ በብርቱ ክትትል መያዙ ሲታይ የሥር ፍርድ ቤቶች ለአመልካች የዋስትና መብት በመከልከላቸው የተፈጸመ መሰረታዊ ስህተት ባለመኖሩ የስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ይጽናልን በማለት ተከራክሯል፡፡አመልካችም የመልስ መልሱን በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

ከላይ አጠር ባለ መልኩ የተገለጸዉ በስር ፍርድ ቤት እና በይግባኝ ሰሚዉ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ እንዲሁም የግራ ቀኙን ክርክር የሚመለከት ሲሆን የአመልካች የዋስትና መብት ጥያቄ ዉድቅ በመደረጉ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የሕግ ስህተት መፈጸም አለመፈጸሙን እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደተመረመረዉም በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 17/2 ስር ማንኛዉም ሰዉ በሕግ ከተደነገገዉ ሥርዓት ዉጭ ሊያዝ፣ክስ ሳይቀርብበት ወይም ሳይፈረድበት ሊታሰር እንደማይችል በመደንገግ ለነጻነት መብት ጥበቃ ተደርጓል፡፡ይህ መብት የሀገራችን የሕግ አካል በሆነዉ በተባበሩት መንግሥታት የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን አንቀጽ 9/1 ላይ በግልጽ እዉቅና የተሰጠዉ መብት ነዉ፡፡እንዲሁም በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 19/6 ስር የተያዙ ሰዎች በሕግ በተደነገጉ ልዩ ሁኔታዎች ፍርድ ቤት የዋስትና መብት ጥያቄዎችን ላይቀበል የሚችልበት ወይም በገደብ መብታቸዉን የሚያስጠብቅበት ሁኔታ ሊኖር የሚችል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በመርህ ደረጃ በዋስ የመፈታት መብት እንዳላቸዉ ተደንግጓል፡፡

የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን የዋስትና መብት ጥያቄ ዉድቅ ያደረገዉ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 67(1/ሀ)ን በመጥቀስ የወንጀሉ አፈጻጸም ከባድ በመሆኑ አመልካች በማስረጃ ተረጋግጦ ጥፋተኛ የሚባል ከሆነ የሚወሰንበትን የቅጣት ዉሳኔ በመፍራት የዋስትና ግዴታዉን አክብሮ ሊቀርብ አይችልም፡፡ አመልካች ፈጽመ ተብሎ የተከሰሰበትን ወንጀል የሚመለከተዉ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 590(1/ሀ እና 2/ሐ) ከአምስት ዓመት እስከ አሥራ አምስት ዓመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ሲሆን የዋስትና መብት የማያስከለክል ድንጋጌ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡አመልካች የተከሰሰበት ይህ ድንጋጌ የዋስትና መብት የማያስከለክል ከሆነ የአመልካች የዋስትና መብት ተቀባይነት ሊያገኝ የማይችለዉ በሕግ የተደነገገዉ ልዩ ሁኔታ መኖሩ ሲረጋገጥ ነዉ፡፡ከዚህ አንጻር ሊጠቀስ የሚችለዉ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 67 ስር የተደነገጉ ሁኔታዎች ናቸዉ፡፡ በዚህ ድንጋጌ ላይ ተለይተዉ የተደነገጉት ሁኔታዎች የዋስትና መብት ሳለመፍቀድ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

በልዩ ሁኔታ የተደነገጉ እንደመሆናቸዉ በተረጋገጡ ሁኔታዎች ላይ ተመስርቶ በጠባቡ ሊተረጎሙና ተግባራዊ ሊሆኑ የሚገባቸዉ ናቸዉ፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ከፍ/ብ/ሥ/ሥሕግ ቁጥር 67/ሀ አተገባበር ጋር በተያያዘ በሰ/መ/ቁጥር 134328 እና 269430 ላይ በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ እንደተመለከተዉ የዋስትና መብት የሚነፈግባቸዉ ምክንያቶች ፍርድ ቤቶች ከተለያዩ ሁኔታዎች አንጻር እየተመለከቱ ሊመዝኗቸዉ እንደሚገባ፤አንድ ተከሳሽ የዋስትና መብት ቢከበርለት ግዴታዉን የሚፈጽም የማይመስል ነዉ ተብሎ ግምት የሚወሰደዉ በቂና ሕጋዊ ሊባሉ በሚችሉ ምክንያቶች ሊሆን እንደሚገባ፤እንዲሁም ምክንያቶቹ በቂና ሕጋዊ ናቸዉ የሚለዉ ጉዳይ ከተለያዩ አከባቢያዊ ሁኔታዎችና ከጉዳዩ ልዩ ባህርይ አንጻር ፍርድ ቤቱ ሊገነዘበዉ የሚችለዉ ጉዳይ እንደሆነ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ የአመልካች የዋስትና መብት ተቀባይነት ያጣዉ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 67/ሀን በመጥቀስ ከወንጀሉ አፈጻጸም ክብደት የተነሳ አመልካች የሚወሰንበትን ቅጣት በመፍራት በዋስትና ወረቀት የተመለከተዉን ግዴታ አክብሮ በየቀጠሮዉ ቀን ሊቀርብ አይችልም የሚል ግምት በመዉሰድ ነዉ፡፡ ሆኖም ይህ በስር ፍርድ ቤት የተወሰደዉና በይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ተቀባይነት ያገኘዉ ግምት ለእዉነታ በተቃረበ በቂ ምክንያት ላይ የተመሰረተ ነዉ ወይ የሚለዉ ከላይ ከተገለጹት መመዘኛዎች አንጻር ሊመረመር ይገባል፡፡አመልካች የወንጀል ምርመራ በሚደረግበት ጊዜ የዋስትና መብቱ ተጠብቆለት እንደነበርና ክሱ ሲመሰረትበም አመልካች መጥሪያ ደርሶት ችሎት ቀርቦ የክስ ሂደቱን መከታተል መጀመሩን በመግለጽ ለዚህ ችሎት ያሰማዉን ተጠሪ አልካደም፡፡ ይህም አመልካች የዋስትና ግዴታዉን እንደሚያከብር የሚያሳይ እንጂ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 67/ሀ ስር እንደተደነገገዉ አመልካች የዋስትና ግዴታዉን አያከብርም የሚል ግምት የሚያስወስድ አይደለም፡፡አመልካች የመከላከያ ደንብ ልብስ በመልበስ ወንጀል ፈጽሟል በሚል በክሱ ዝርዝር ላይ አለመገለጹን የስር ፍርድ ቤት አረጋግጧል፡፡ በመሆኑም የወንጀሉ አፈጻጸም ከባድ ነዉ የሚለዉ ምክንያት ሌላ ተጨማሪ ደጋፊ ምክንያት በሌለበት የዋስትና መብት ለማስከለከል ሊያገለግል የሚችል ምክንያት አይደለም፡፡

በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን የዋስትና መብት ጥያቄ ዉድቅ በማድረግ የወሰነዉና በይግባኝ ሰሚ ችሎት በትዕዛዝ የጸናዉ ዉሳኔ ከላይ በተጠቀሱት መዛግብት ላይ የተሰጠዉን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም እና የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 67/ሀን አተገባበር ባልተከተለ አኳኋን የአመልካችን ሕገ መንግሥታዊ ጥበቃ ያለዉን የዋስትና መብት ያለበቂና ተጨባጭ ምክንያት የሚነፍግ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሀ እና ሸ) እና 10(1/ለ) መሰረት ሊታረም የሚገባዉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ዉሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 327881 ላይ በቀን 27/02/2017ዓ/ም የሰጠዉ ትዕዛዝ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 272030 ላይ በቀን 19/03/2017 ዓ.ም የሰጠዉ ትእዛዝ በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 መሰረት ተሽረዋል፡፡

2. አመልካች የተከሰሰበት ወንጀል የዋስትና መብት የሚያስከለክል ካለመሆኑም በተጨማሪ በልዩ ሁኔታ የዋስትና መብት ለመንፈግ የሚያስችል በቂ ምክንያት ባለመኖሩ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ብር 50,000.00(ሃምሳ ሺህ ብር) ሲያስቀምጥ ወይም ለዚህ በቂ የሆነ የሰዉ ዋስ ወይም መያዣ ሲያቀርብ በዋስትና ከእስር እንዲፈታ ተወስኗል፡፡

## ትእዛዝ

1. በዚህ ዉሳኔ መሠረት እንዲፈጽም የዉሳኔዉ ግልባጭ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ግልባጩ ለግራ ቀኙም ይሰጣቸዉ፡፡

2. መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይተላለፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

# በየካቲት ወር 2017 የተወሰኑ
# <u>28</u> የሰበር ችሎት ውሳኔዎች

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 243564

የካቲት 27 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ገበየሁ ፈለቀ

ዓለማየሁ ሹናራ

ደረጀ አያና

ኑረዲን ከድር

ብርሃኑ መንግሥቱ

አመልካች፡ አቶ ጉዕሽ ካሳ ደሞዝ አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡ 1. አቶ አማኑኤል ወልደሊባኖስ ተስፋዬ
2. አቶ ዳዊት አብርሃ
3. አቶ ፊሊጶስ ጥላሁን
} አልተጠሩም

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ዉሳኔ

ጉዳዩ ዳግም ዳኝነት የሚታይበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ክርክሩ የተጀመረው አመልካች በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የዳግም ዳኝነት አቤቱታ በማቅረባቸው ሲሆን ችሎቱ ክርክሩን መርምሮ ለሰጠዉ ዉሳኔ መነሻ ያደረገዉ ተጠሪዎች ለስር ፍርድ ቤት ያቀረቡትን የሰነድ ማስረጃዎች መሆኑን፤ነገር ግን የኢትዮጵያ ብረታ ብረት ኮርፖሬሽን ለአመልካች ድርጅት ብር 17,500,000.00 መክፈሉን ለማረጋገጥ በይግባኝ ሰሚዉ ችሎት በመ/ቁጥር 211132 እና በመ/ቁጥር 211227 ላይ ይግባኝ

ያቀረቡት የአሁን ተጠሪዎች ለስ ፍርድ ቤት በማስረጃነት ያቀረቡት የሰነድ ማስረጃ ሐሰተኛ ስለመሆኑ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 249579 ላይ በቀን 16/10/2014 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ ማረጋገጡን በመዘርዝር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥርር 6 መሠረት ዳግም ዳኝነት እንዲታይላቸዉ ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪዎችም ለአቤቱታዉ መልሱ እንዲሰጡ ታዘዉ በመ/ቁጥር 249579 ላይ የተባለዉ ሰነድ ሐሰተኛ መሆኑን የሚያረጋጥ ውሳኔ ስላልተሰጠ የአመልካች ዳግም ዳኝነት ይታይልኝ አቤቱታ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም ከፍ ሲል በተመለከተዉ መሠረት የቀረበዉን ይግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ በቀን 28/04/2015ዓ/ም በሰጠዉ ብይን አመልካች በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በነበረዉና በመ/ቁጥር 249579 በታየዉ የሙስና ወንጀል ክስ 14ኛ ተከሳሽ የነበሩ ሲሆን በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠዉ የዉሳኔ ይዘት ላይ እንደተመለከተዉ አመልካች ከኢትዮጵያ ብረታ ብረት ኮርፖሬሽን አመራሮችና ሠራተኞች በፈጸሙት ከባድ የሙስና ወንጀል አመልካች በልዩ ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን የሙስና ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ነዉ፡፡በወንጀል ክሱ ላይ የአመልካች ድርጊት ነዉ ተብሎ የተጠቀሰዉም የአመልካች ድርጅትን ጨምሮ ለተለያዩ ንዑስ ተቋራጮች የህዳሴ ግድብ ዉሃ የሚተኛበትን ቦታ የምንጣሮ ሥራ እንዲሠሩ በዉል ከወሰደ በኋላ የአመልካች ድርጅት ለሠራዉ የምንጣሮ ሥራ ሊከፈለዉ ከሚገባዉ ክፍያ በላይ ገንዘብ እንዲከፈለዉ በማድረግ የብረታ ብረት ኮርፖሬሽን ገንዘብ እንዲመዘበር በተደረገዉ ወንጀል ተካፋይ ሆነዋል በሚል ነዉ፡፡ዐቃቤ ሕግ ክሱን ለማስረዳት ልዩ ልዩ ሰነዶችን በማስረጃነት ያቀረበ ቢሆንም 1ኛ ተጠሪ በዳግም ዳኝነት አቤቱታቸዉ ላይ የጠቀሱት የብር 17,500,000.00 ክፍያ የተከፈለበትን ሰነድ በማስረጃነት ስለማቅረቡ በመ/ቁጥር 249579 ላይ በቀን 16/10/2014ዓ/ም የተሰጠዉ ዉሳኔ አያመላክትም፡፡ይህ ብቻ ሳይሆን በእርግጥ አመልካች ከቀረበባቸዉ የሙስና ወንጀል ክስ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 149/2 በነጻ የተሰናበቱ ቢሆንም የተሰናበቱበት የአመልካች ድርጅት ከሠራዉ የምንጣሮ ሥራ በላይ የተከፈለዉ ገንዘብ ስለመኖሩ አልተረጋገጠም በሚል እንጂ ብር 17,500,000.00 አልተከፈላቸዉም ወይም ይህ ሰነድም ሀሰተኛ ሰነድ መሆኑ አልተረጋገጠም፡፡ አንድ ሰዉ በደግም ዳኝነት እንዲታይ አቤቱታ ሊቀርብ የሚገባው በወንጀል ተግባር ወይም መደለያን መሰረት በማድረግ በተዘጋጀ ሀሰተኛ ማስረጃ የተሰጠ ውሳኔ ከሆነ ብቻ እንደሆነ የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 6(1/ሀ) ይደነግጋል፡፡አመልካች ግን ከቀረበባቸው የሙስና ወንጀል በነፃ መሠናበታቸዉን መነሻ በማድረግ ነው እንጂ የጠቀሱት የሠነድ ማስረጃ ሀሰተኛ እና በወንጀል ድርጊት የተሰራ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ያላቀረቡ በመሆኑ ዳግም ዳኝነት ሊታይ አይገባም በማለት በአብላጫ ድምፅ አቤቱታውን ውድቅ አደርጓል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

አመልካች በጠበቃቸዉ አማካኝነት በቀን 27/06/2015 ዓ.ም በ11 ገጽ የተፃፈ የሰበር አቤቱታቸውን ያቀረቡት ከላይ በተገለፀው አግባብ በተሰጠዉ ብይን መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም በአጭሩ - አመልካች ከአቤቱታዉ ጋር በማያያዝ ያቀረቡት የሰነድ ማስረጃዎች እና በፍርድ ቤቱ በኩል እንዲቀርቡላቸዉ የጠየቋቸዉ ሰነድ ማስረጃዎች እንዲሁም ፍርድ ቤቱ በራሱ ተነሳሽነት ሊያስቀርባቸዉ የሚገቡ ሌሎች የሰነድ ማስረጃዎች ሁሉ ዳግመኛ ዳኝነት ሊታይ ይገባል ለማለት በቂ ሆነዉ እያለ ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ማስረጃዎቹ ፍርዱ የወንጀል ተግባርናና ሐሰተኛ ማስረጃን መሠረት በማድረግ መወሰኑን አያሳዩም በማለት ዉድቅ ማድረጉ መሰረታዊ ስህተት ነዉ፡፡ የኢትዮጵያ ብረታ ብረት ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ለጂ.ጂ.ጂ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኃላ/የተ/የግ/ማኅበር ብር 17,500,000.00 መክፈሉን ለማረጋገጥ ኒዉ ዴቨሎፐመንት /በኒዉ ቢዝነስ ኮርፖሬት ቀርቧል የተባለዉ ሰነድ በጠቅላላዉ በሐሰት ተዘጋጅቶ የቀረበ ሀሰተኛ ሰነድ መሆኑን የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 249579 ላይ በቀን 16/10/2014ዓ/ም በሰጠዉ ፍርድ የተረጋገጠ ሆኖ እያለ ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት አቤቱታዉን አለአግባብ ዉድቅ አድርጓል፡፡አመልካች አቤቱታዉን ያረጋግጡልኛል በማለት በመ/ቁጥር 249579 ላይ እና በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን አይናችን ፕሮግራም ላይ የተላለፈዉን ፕሮግራም በመጥቀስ እንዲቀርብላቸዉ ቢጠይቁም እንዲቀርቡ ሳያደርግ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መ/ቁጥር 210313፣ 2100580፣ 205193 እና 161772 የሆኑ መዛግብት አስቀርቦ ሳይመረምር አቤቱታዉን በብይን ዉድቅ ማድረጉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 6 እና 145 ላይ የተደነገገዉን እንዲሁም በሰ/መ/ቁጥር 52546 ላይ የተሰጠዉን የሕግ ትርጉም የሚቃረን ነዉ፡፡አመልካች የሠነዱን ሀሰተኛነት አስቀድሜ ማወቅ አለመቻሌን አስረድቻለሁ፡፡በፍርድ ሂደቱ አስቀድሜ ባውቅ ኖሮ ለፍርዱ መለወጥ በቂ ምክንያት ሊሆኑ ይችሉ እንደነበር በአቤቱታው ላይ አስረድቻለሁ፡፡ ስለሆነም የዳግም ዳኝነት አቤቱታ ያቀረብኩት ፍርዱን ሊያስለውጥ በሚችል ሀሰተኛ ማስረጃ እና ወንጀል ጠቀስ ተግባሮች መሰረት የተሠጠ ውሳኔ መሆኑን በሚያረጋግጥ መልኩ በመሆኑ የይግባኝ ሰሚዉ ብይን ተሽሮ ዳግም ዳኝነት ሊታይ ይገባል ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

ሰበር አጣሪ ችሎት የአመልካች ዳግም ዳኝነት ጥያቄ ሊታይ አይገባም ተብሎ በይግባኝ ሰሚዉ ችሎት በተሰጠዉ ብይን ላይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት መፈጸም አለመፈጸሙ እንዲመረመር ጉዳዩን ለሰበር ችሎት መርቶታል፡፡

ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታዉን እና የይግባኝ ሰሚዉን ችሎት ብይን መርምሮ በቀን 25/11/2016 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት በአብላጫ ድምጽ በሰጠዉ ትእዛዝ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በተሰጠ ብይን ላይ በሦስተኛ ተራ ቁጥር ላይ የተሰየሙት ዳኛ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ደረጃ ተሰይመዉ ለመዳኘት የሚያስችላቸው የዳኝነት ስልጣን አላቸው ወይስ የላቸዉም? ውሳኔው በተሟላ የዳኞች ቁጥር የተሰጠ ነዉ ወይ? የሚሉ ጭብጦችን ከሕገ-መንግሥቱ አንቀፅ 55/13፣81/2፣ከአዋጅ ቁጥር 1233/2013 እና በሰ/መ/ቁጥር 250725 (ያልታተመ) ላይ ከተሰጠዉ የሕግ ትርጉም አንጻር ለመመርመር

በሚል ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ አዝዟል፡፡ይህ ትእዛዝ ከተሰጠ በኋላ የተጠሪዎች ጠበቃ በቀን 30/01/2017 ዓ/ም በተጻፈ አቤቱታ የአመልካች ሰበር አቤቱታ ከመጥሪያ ጋር ስላልደረሰን አቤቱታዉ እንዲደርሰን እና መልሳችንን እንድንሰጥ ይታዘዝልን በማለት ጠይቀዉ በአቤቱታዉ ላይ ትእዛዝ ለመስጠት በሚል ሲቀጠር እንደቆየ ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡

ችሎቱ ከላይ የተያዘዉን ጭብጥ እና የአመልካችን የሰበር አቤቱታ በመመርመር ተጠሪዎችን ሊያስቀርብ በሚችል ደረጃ በይግባኝ ሰሚዉ ችሎት በተሰጠ ብይን ላይ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የሕግ ስህተት መፈጸም አለመፈጸሙን በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 80(1/ሀ) እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2/4 እና 10(1/ለ) ስር ከተደነገጉት መመዘኛዎች አንጻር መርምሯል፡፡

በመጀመሪያም በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በተሰጠ ዉሳኔ ላይ በሦስተኛ ተራ ቁጥር ላይ የተሰየሙት ዳኛ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ደረጃ ተሰይሞ ለመዳኘት የሚያስችላቸው የዳኝነት ስልጣን አላቸው ወይስ የላቸዉም? ውሳኔው በአሰያየም ረገድ በተሟላ የዳኞች ቁጥር የተሰጠ ነዉ ወይ? በሚል የተያዘዉን ጭብጥ መርምረናል፡፡ችሎቱ ይህንን ጭብጥ በአብላጫ ድምጽ በሰጠዉ ትእዛዝ የያዘዉ ከሕገ-መንግሥቱ አንቀፅ 50/13 እና 81/2፣ከአዋጅ ቁጥር 1233/2013 እና በሰ/መ/ቁጥር 250725 (ያልታተመ)ላይ ከተሰጠዉ የሕግ ትርጉም አንጻር ለመመርመር ቢሆንም ለዚህ ጭብጥ መያዝ ዋነኛ መሠረት የሆነዉ በሰ/መ/ቁጥር 250725 ላይ የተሰጠዉ የሕግ ትርጉም ነዉ፡፡ይህ የሕግ ትርጉም በአብላጫ ድምጽ የተወሰነ ሲሆን የተሰጠዉም የሕግ ትርጉም በአጭሩ *"...ዳኛ መሆን የሚቻለው በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ብቻ በሚሰጥ ሹመት በመሆኑ አሁን በተያዘው ጉዳይ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተሰይመው ውሳኔ ከሰጡ ዳኞች መካከል በሦስተኛ ተራ ቁጥር ላይ የተሰየሙት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኝነት ሹመት ያልተሰጣቸው በመሆኑ ችሎቱ በሕግ ከተወሰነለት ቁጥር በታች በሁለት ዳኞች ውሳኔ መስጠቱን ያሳያል፡፡ ይሕም በሕግ የተመለከተው የዳኞች ቁጥር ሳይሟላ ውሳኔ እንደተሰጠ የሚያስቆጥር ነዉ፡፡በሰ/መ/ቁጥር 73696 (ቅጽ 13) ላይ የዳኞች ቁጥር ሳይሟላ የሚሠጠው ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ ሕጋዊ ውጤት ሊኖረው የሚገባ አይደለም በማለት አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ተሰጥቷል፡፡ ስለሆነም በዚህም ጉዳይ ዉሳኔ የተሰጠዉ የዳኞች ቁጥር ሳይሟላ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡"* የሚል ነዉ፡፡

ነገር ግን በሰ/መ/ቁጥር 250725 ላይ የተጠቀሰዉ የሕግ ትርጉም ከተሰጠ በኋላ ይህ የሕግ ትርጉም ሰባት ዳኞች በተሰየሙበት በሰ/መ/ቁጥር 242695 ላይ በቀን 04/02/2017ዓ/ም በተሰጠዉ የፍርድ ዉሳኔ "በአዋጅ ቁጥር 1233/2013 አንቀጽ 26/2 መሰረት በዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የተሰጠው ውሳኔ ዳኞችን በጊዜያዊነት ከአንድ ደረጃ ፍርድ ቤት ወደሌላ ደረጃ ፍርድ ቤት አዛውሮ ማሰራት እንጂ የዳኝነት ሹመት ባለመሆኑ እና በሕግ አውጪው በወጣና ጸንቶ ባለ ሕግ በተሰጠ ሥልጣን መሰረት የተከናወነ ሕጋዊ ተግባር በመሆኑ

በዝውውር በጊዜዊነት የተመደቡ ዳኛ በተሰየሙበት ችሎት የተሰጠው ውሳኔ ባልተሟላ ዳኛ የተሰጠ ዉሳኔ ነዉ ሊባል አይችልም።" በሚል አስገዳጅ የሕግ ትርጉም እንዲለወጥ ወይም እንዲተካ ተወስኗል።ስለሆነም በተያዘዉ ጉዳይ በሰ/መ/ቁጥር 250725 ላይ ከተሰጠዉ የሕግ ትርጉም አንጻር ለመመርመር ጭብጥ ተይዞ የነበረ ቢሆንም ጭብጡ እንዲመሠረት ምክንያት የሆነዉ የሕግ ነጥብ ወይም በአብላጫ ድምጽ አምስት ዳኞች በተሰየሙበት ሰበር ችሎት ተሰጥቶ የነበረዉ የሕግ ትርጉም በሰ/መ/ቁጥር 242695 ላይ በተሰጠ የሕግ ትርጉም የተለወጠ እና የተያዘዉም ጭብጥ በዚሁ አግባብ ምላሽ ያገኘ በመሆኑ በዚህ ረገድ የተያዘዉን ጭብጥ የተጠሪዎችን መልስ መጠበቅ ሳያስፈልግ ዉድቅ በማድረግ አልፈነዋል።

በመቀጠል አመልካች በይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 211132 እና 211227 ላይ የተሰጡት የፍርድ ዉሳኔዎች በሐሰተኛ ማስረጃ ላይ ተመስርቶ የተሰጡ ዉሳኔዎች መሆናቸዉን የሚያሳይ አዲስ ማስረጃ አግኝቻለሁ በማለት ዳግመኛ ዳኝነት እንዲታዩልኝ ያቀረብኩት አቤቱታ ዉድቅ ተደርጎ በተሰጠዉ ብይን መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ ከይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ብይን እና አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል።

እንደመረመርነዉም የፍትሐ ብሔር ክርክር እንደማንኛዉም ክርክር በአንድ የክርክር ደረጃ በሥነ ሥርዓት ሕጉ በተደነገገዉ አግባብ የመጨረሻ እልባት አግኝቶ መቋጨት አለበት። ክርክሮች የመጨረሻ ዉሳኔ ካገኙ በኋላ በዚያዉ አስቀድሞ የመጨረሻ ዉሳኔ ባገኘ ሥረ ነገር እና ጭብጥ ላይ አስቀድሞ በተከራከሩ ወገኖች መካከል ተደጋጋሚ ክርክር የሚደረግ ከሆነ የተከራካሪ ወገኖችንና የፍርድ ቤቶችን ጊዜ፣የሰዉና የቁስ ሀብት (Judicial Economy) ይባክናል እርስ በእርስ የሚጣረሱ ዉሳኔዎች የሚሰጥበትንም አለአስፈላጊ አጋጣሚ ይፈጥራል።ይህ እንዳይሆን የሥነ ሥርዓት ሕጉ የመጨረሻ ዉሳኔ ባገኘ ጉዳይ ላይ ድጋሚ አዲስ ክስ እንዳይቀርብ የሚከላከል የመጨረሻ ዉሳኔ ያገኙ ጉዳዮችን የሚመለከት መርህ *(Priniciple of Res Judicata)* በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5 ስር ተደንግጓል። በመሆኑም ክርክሮች የመጨረሻ ዉሳኔ ካገኙ በኋላ በመርህ ደረጃ በድጋሚ እንዲታዩ የሥነ ሥርዓት ሕጉ አይፈቀድም። በልዩ ሁኔታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 6 ስር የተደነገጉት ዉስን ሁኔታዎች ሲኖሩ አንድ ጉዳይ የመጨረሻ ዉሳኔ ካገኘ በኋላ ዳግመኛ ዳኝነት የሚታይበት ሥነ ሥርዓት ተዘርግቷል። ዳግመኛ ዳኝነት ሥነ ሥርዓት በመፈቀዱ ክርክሮች በየደረጃዉ ባሉ ፍርድ ቤቶች በተለያየ የክርክር ደረጃ እየታዩ የሥነ ሥርዓት ሕጉ ዓላማ ሳይሳካ እንዳይቀር ይህ ልዩ ሁኔታ በጠባቡ ተግባራዊ እንዲደረግ በሚያስችል መልኩ የሥነ ሥርዓት ሕጉ ሥርዓት ዘርግቷል።

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 6(1/ሀ) መሰረት አንድ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ በዳግመኛ ዳኝነት ሊታይ የሚችለዉ ይህ የመጨረሻዉ ፍርድ ወይም ዉሳኔ ወይም ትእዛዝ የተሰጠዉ በሐሰት ተዘጋጅቶ የቀረበዉን ሰነድ ወይም ሐሰተኛ የምስክርነት ቃልን ወይም መደለያን ወይም ወንጀል ጠቀስ የሆነ ተግባርን መሰረት በማድረግ እንደሆነ የሚያረጋግጥ አዲስ ማስረጃ በተከራካሪ ወገን ሲገኝ እና አቤት ባዩ ተከራካሪ ወገን ከፍርድ በኋላ አገኘሁኝ ያለዉ አዲስ ማስረጃ መኖሩን ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት አስፈላጊዉን ትጋት አድርጎ ለማወቅ

ያለመቻሉን ማስረዳት ሲችል ነዉ፡፡ከዚህም በተጨማሪ በዚሁ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ ፊደል “ለ” ላይ እንደተደነገገዉ አዲስ የተገኘዉ ማስረጃ የዉሳኔዉን መሰረታዊ ይዘት የሚነካ (Substantially affects the merit of the case) መሆን ይኖርበታል፡፡ እንዲሁም አቤት ባዩ አቤቱታዉን አዲስ ማስረጃ ካገኘበት ወይም መኖሩን ካወቀበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ዉስጥ ማቅረብ እንዳለበት እና አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤት ዳግመኛ ዳኝነት ሊታይ ይገባዋል ወይም አይገባዉም ሲል የሚሰጠዉ ዉሳኔ ላይ ይግባኝ ለማቅረብ እንደማይቻል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 6(2 እና 4) ስር ተመልክቷል፡፡

አመልካች ለይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ያቀረቡት አቤቱታ በተጠቃሾቹ መዛግብት ላይ ችሎቱ ሰጥቶ የነበረዉን የፍርድ ዉሳኔ የሰጠዉ በሀሰተኛ ማስረጃ ላይ ተመስርቶ መሆኑን በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሚገኝ ወንጀል ችሎት ላይ በመ/ቁጥር 249579 ላይ በቀን 16/10/2014ዓ/ም የተሰጠዉ ፍርድ ያሳያል፡፡እንዲሁም ችሎቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 145 መሰረት ተጨማሪ ማስረጃ አስቀርቦ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 6 መሰረት ዳግም ዳኝነት አይቶ አስቀድሞ በመ/ቁጥር 211132 እና 211227 ላይ በሆኑ መዛግብት ላይ የሰጠዉን የፍርድ ዉሳኔ እንዲሽርልኝ በማለት በመጠየቃቸዉ ነዉ፡፡ተጠሪዎች በሰጡት መልስ ያቀረብናቸዉ ማስረጃዎች ሐሰተኛ መሆናቸዉን የሚያሳይ ፍርድ ስላልተሰጠ አቤቱታዉ ዉድቅ ሊሆን ይገባል በማለት መከራከራቸዉን የይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ብይን ያሳያል፡፡ የግራ ቀኙን ክርክር የመረመረዉ ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት አመልካች ያቀረቡት ማስረጃ በሐሰተኛ ማስረጃ ላይ ተመስርቶ ዉሳኔ መሠጡትን የሚያሳይ አይደለም በማለት የዳግም ዳኝነት ጥያቄዉን ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

አመልካች አዲስ ያገኙሁት ነዉ በማለት በይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ትእዛዝ እንዲቀርብላቸዉ የጠየቁት ማስረጃ ተጠሪዎች ከኢትዮጵያ ብረታ ብረት ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ለጂ.ጂ.ጂ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኃላ/የተ/የግ/ ማኅበር ብር 17,500,000.00 መክፈሉን ለማስረዳት ያቀረቡት የሰነድ ማስረጃዎች ሐሰተኛ መሆናቸዉን የሚያስረዳ ማስረጃ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሚገኙ የተለያዩ መዛግብት ዉስጥ ይገኛሉ ያሉትንና በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን አይናችን ፕሮግራም ማስረጃ እንዲቀርብ ጠይቀዉ ችሎቱ ሳያስቀርብ አቤቱታዬን ዉድቅ አድርጎብኛል በማለት ነዉ፡፡ በአንድ የፍትሐ ብሔር ክርክር ተከራካሪ በእጁ የሚገኘዉንና በእጁ የማይገኘዉን ወይም በሌላ አካል ዘንድ የሚገኘዉን ማስረጃ በሥነ ሥርዓት ሕጉ በተዘረጋዉ አግባብ በክርክሩ ሂደት ማቅረብና በፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ከፍርድ በፊት ማስቀረብ ይኖርበታል፡፡በዚህ አግባብ በክርክሩ ሂደት በሥነ ሥርዓት ሕጉ አግባብ ማቅረብ የሚቻል ማስረጃ ሳያቀርቡ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ አዲስ ማስረጃ ተገኝቷል በሚል ፍርዱ በዳግመኛ ዳኝነት ሥነ ሥርዓት እንደገና እንዲመረመር መጠየቅ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ በቁጥር 6 ስር በተዘረጋዉ ሥነ ሥርዓት ለማሳካት ከተፈለገዉ ዓላማና መንፈስ ዉጭ ስለሚሆን ተቀባይነት ያለዉ አይደለም፡፡ለዚህም ነዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 6(1/ሀ) ላይ *አቤት ባዩ ተከራካሪ ወገን ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት አስፈላጊዉን ትጋት አድርጎ ከፍርድ በኋላ አገኘሁኝ ያለዉ አዲስ ማስረጃ መኖሩን ለማወቅ ያለመቻሉን ማስረዳት* የገባዋል ተብሎ የተደነገገዉ፡፡አመልካች በይግባኝ ሰሚዉ

ችሎት ትእዛዝ እንዲቀርቡ ጠይቄያለሁ ያሉት በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተለያዩ መዛግብት ዉስጥ ይገኛሉ ያሏቸዉ ማስረጃዎችም ሆነ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን አይናችን ፕሮግራም ተጠሪዎች አቅርበዉ የነበሩት የሰነድ ማስረጃዎች ሐሰተኛ መሆናቸዉን የሚያስረዱ ከሆኑ ከጠሪዎች ጋር የነበራቸዉ ክርክር ላይ ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት ተገቢዉን ትጋት አድርገዉ ራሳቸዉ ማስረጃዎችን ማቅረብ አሊያም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ ሕግ ቁጥር 145 ስር በተደነገገዉ አግባብ በፍርድ ቤቱ ትእዛዝ እንዲቀርብላቸዉ መጠየቅ ሲገባቸዉ ይህንን ሳያደርጉ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ አዲስ እንደተገኙ ማስረጃዎች በፍርድ ቤት ትእዛዝ እንዲቀርቡና በዳግመኛ ዳኝነት እንዲመረመሩ እንዲጠይቁ የሥነ ሥርዓት ሕጉ አይፈቅድላቸዉም፡፡ እንዲህ አይነት ማስረጃ አስቀድሞ መኖሩ የማይታወቅ ከፍርድ በኋላ መኖሩ የታወቀና የተገኘ አዲስ ማስረጃ ነዉ ሊባል የማይችል በመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 6(1/ሀ) ስር የተደነገገዉን መስፈርት የሚያሟላ አይደለም፡፡ በተጨማሪም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 6(1/ሀ) ላይ *አቤት ባዩ ተከራካሪ ወገን ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት አስፈላጊዉን ትጋት አድርጎ ከፍርድ በኋላ አገኘሁኝ ያለዉ አዲስ ማስረጃ መኖሩን ለማወቅ ያለመቻሉን ማስረዳት* የሚለዉ የሕጉ አነጋገር የሚያስረዳዉ በክርክሩ ወቅት የነበረ ማስረጃን ሆኖ ነገር ግን አስፈላጊዉ ትጋት ተደርጎ ከፍርድ በኋላ መኖሩ የታወቀዉን አዲስ ማስረጃ መሆኑን እንጂ በአመልካች እና በተጠሪዎች መካከል በነበረዉ ክርክር ላይ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ የተፈጠረ ማስረጃን የሚያካትት ባለመሆኑ አመልካች ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ሰጥቶ መመርመር ነበረበት ያሉት ተጠቃሾቹ ማስረጃዎች እንዲቀርቡ ተደርጎ አለመመርመሩ ሥነ ሥርዓታዊ ነዉ ከሚባል በስተቀር የተፈጸመ ስህተት የለም፡፡

እንዲሁም አመልካች ለጂ.ጂ.ጂ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኃላ/የተ/የግ/ማኅበር ብር 17,500,000.00 አልተከፈለዉም በማለት ከተጠሪዎች ጋር ሲከራከሩና ስለመከፈሉ ለማስረዳት ተጠሪዎች በማስረጃነት ያቀረቡት የሰነድ ማስረጃዎች ሐሰተኛ ናቸዉ የሚል አቋም ካላቸዉ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 249579 ላይ የሙስና ወንጀል ክስ ቀርቦባቸዉ በቀን 16/10/2014ዓ/ም በተሰጠ ዉሳኔ በነጻ እስከሚሰናበቱ መጠብ ሲገባቸዉ በተጠሪዎች የፍትሐ ብሔር ክስ በቀረበባቸዉ መዛግብት ላይ ሐሰተኛ መሆናቸዉን በመግለጽ በፎሬንሲክ እንዲመረመሩ በማድረግ ማስረዳት እየቻሉ ይህንን ሳያደርጉ ቆይተዉ የወንጀል ጉዳይ በታየበት መዝገብ ዉስጥ ሀሰተኛ መሆናቸዉን የሚያሳይ ማስረጃ ስለሚገኝ ቀርቦ ይታይልኝ የሚለዉ ክርክር ዳግመኛ ዳኝነት ሥነ ሥርዓት ተግባራዊ እንዲሆን ሕጉ የፈለገበትን ዓላማ ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት ያለዉ አይደለም፡፡በወንጀል መ/ቁጥር 248579 ላይ አመልካችን አስመልክቶ የተሰጠዉ ዉሳኔም ተጠሪዎች በፍትሐ ብሔር ክርክር ለአመልካች ድርጅት ብር 17,500,000.00 እንደተከፈለ ለማስረዳት ያቀረቡት የሰነድ ማስረጃዎች ሐሰተኛ ናቸዉ ተብሎ ዉሳኔ የተሰጠበት እንዳልሆነ ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ከዉሳኔዉ ያረጋገጠዉ ፍሬ ነገር በመሆኑ ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ከዉሳኔዉ ያረጋገጠዉን መሠረት በማድረግ በደረሰበት ድምዳሜ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል ስህተት አልተገኘም፡፡

ማስ ታወሻ፡ - ይህ የ ሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነ ድ ለ ጥና ትና ምር ምር ሥራ ወይም ለ ግን ዛቤ እ ን ጂ ለ ፍር ድ አ ፈጻ ጸ ም ዓ ላ ማ አ ያ ገ ለ ግል ም!

በመሆኑም ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ዳግመኛ ዳኝነት ሊታይ አይገባም በማለት የሰጠዉ ብይን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 6 አተገባበርና ዓላማ የተከተለ ከመሆኑም በተጨማሪ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2/4 እና አንቀጽ 10(1/ለ) ስር ከተደነገጉት መመዘኛዎች አንጻር ሲታይም በዚህ ሰበር ችሎት ታይቶ ሊታረም የሚችል መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ባለመገኘቱ ተጠሪዎችን ማስቀረብ ሳያስፈልግ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 28/2 እና በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 7/1 ስር በተደነገገዉ መሰረት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ዉድቅ አድርገናል፡፡

**<u>ትእዛዝ</u>**

- የስር ፍርድ ቤት መዛግብት ይመለሱ፡፡መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

የሰ/መ/ቁ 244417

የካቲት 25 ቀን 2017ዓ/ም

**ዳኞች፡-** ብርሃኑ አመነዉ

ሽመክት አሰፋ

በዕዉቀት በላይ

መላኩ ካሳዬ

አየለ ማሞ

**አመልካች፡-** አቶ ታዬ ከተማ ደጋጋ - ጠበቃ ታዬ ገ/መድህን ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** 1. አቶ ሙሉጌታ ታደሰ
2. ወ/ሮ ብርቂ ከተማ | አልቀረቡም
3. ወ/ሮ ሹምቡሬ ከተማ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው የገጠር መሬት ይዞታ ዉርስን የተመለከተ ጉዳይ ሲሆን የተጀመረው በሲናና ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍ/ቤት 2ኛ ተጠሪ ከሳሽ፤ አመልካች ተከሳሽ ሲሆኑ 1ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች እንዲሁም አቶ ጉደታ ሽለማ እና አቶ መርጋ ደበላ ጣልቃ ገቦች ነበሩ፡፡ የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 33516 መጋቢት 14 ቀን 2014 ዓ.ም የወረዳዉን ፍ/ቤት በማሻሻል የሰጠዉና በየደረጃዉ ባሉት የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ችሎቶች በተሰጡ ዉሳኔዎች የጸናዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በሚል ነዉ፡፡

2ኛ ተጠሪ በአመልካች ላይ በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት፡- ወላጆቻቸዉ የሆኑት አቶ ከተማ ደጋጋ እና ወ/ሮ ኢቱ በዳኔ እንደ ቅድም ተከተላቸዉ በ2010 ዓ.ም እና በ2011 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፡፡ አመልካችና 3ኛ ተጠሪን ጨምሮ 3 ሰዎች የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች ሲሆኑ ወላጆቻቸዉ በሕይወት በነበሩበት ጊዜ የነበሯቸዉ በክሱ ከተራ ቁጥር 1ኛ እስከ 12ኛ የተዘረዘሩት የገጠር መሬት ይዞታዎች አጠቃላይ ስፋታቸዉ 58 ቀርጥ ሲሆን በአመልካች እጅ የሚገኙ መሆናቸዉን ገልጸዉ የ2ኛ ተጠሪ ድርሻ የሆነዉን 19.3 ቀርጥ እንዲያካፍላቸዉ ጠይቀዋል፡፡

አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስ፡- በተራ ቁጥር 1ኛ፣ 2ኛ፣ 10ኛ እና በ9ኛ ተራ ቁጥር ከተገለጸዉ ዉስጥ 4 ቀርጥ የአመልካች የግል ይዞታ በመሆኑ ከክፍፍሉ እንዲወጣ፤ በተራ ቁጥር 5ኛ እና 7ኛ ላይ የተጠቀሱ ይዞታዎች በስር ፍ/ቤት 3ኛ ጣልቃ ገብ የነበሩት የአቶ ጉደታ ሽለማ ነዉ፡፡ በክሱ ተራ ቁጥር 3ኛ፣ 4ኛ እና 6ኛ ላይ የተጠቀሱት ይዞታዎች የዉርስ ይዞታዎች ናቸዉ ተብሎ ቢወሰን እንደማይቃወም በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡

1ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችን ጨምሮ በስር ፍ/ቤት ጣልቃ ገብ የነበሩ ከዉርስ ይዞታዉ በወራሽነትና በተተኪ ወራሽነት ድርሻ እንደሚገባቸዉ እንዲሁም 3ኛ ጣልቃ ገብ በክሱ ተራ ቁጥር 5ኛ እና 7ኛ የተገለጹት ይዞታዎች የግሉ ይዞታዎች መሆናቸዉን በመግለጽ ከዉርሱ ይዞታ ዉጪ እንዲደረጉ በመጠየቅ ተከራክረዋል፡፡

አመልካች ለጣልቃ ገብ አቤቱታዉ በሰጡት መልስ በክሱ 1ኛ፣ 2ኛ፣ 8ኛ፣ 10ኛ፣ 11ኛ፣ 12ኛ እና 9ኛ ተራ ቁጥር ከተጠቀሰዉ 5 ቀርጥ ይዞታ ላይ ሟቾች መብት አልነበራቸዉም፡፡ በጎጆ መዉጫነት በግሉ ሰጥተዉት ለ30 ዓመት ለሚሆን ጊዜ ሲጠቀምበት የነበረ ይዞታ በመሆኑ የግሉ ነዉ ተብሎ እንዲወሰን በመጠየቅ ተከራክሯል፡፡

የሲናና ወረዳ ፍ/ቤት ቤትም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ መርምሮ፡- የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ አባት አያቶቹን ቀድሞ ስለሞተ እንዲሁም የስር 4ኛ ጣልቃ ገብ አባት ከአያቶቹ መሞት ቀድሞ ዉትድርና በሄደበት ያልተመለሰ በመሆኑ አባቶቻቸዉን ተክተዉ አያቶቻቸዉን ሊወርሱ አይገባም፡፡ 3ኛ ጣልቃ ገብ በሕጋዊ መንገድ ጉዲፈቻ ያደገ መሆኑ ስላልተረጋገጠ የወርስ ይዞታዉ ማይገባዉ ቢሆንም በተራ ቁጥር 5ኛ እና 7ኛ የተጠቀሱት ይዞታዎች በስጦታ ያገኛቸዉ ስለሆኑ የዉርስ

ይዞታ አይደሉም፡፡ በክሱ ተራ ቁጥር 1ኛ፣ 2ኛ፣ 9ኛ እና 10ኛ የተገለጹት ይዞታ በጎጆ መዉጫነት የተሰጡትና በስሙ የተመዘገቡ ስለሆነ የግል ይዞታዉ ናቸዉ፡፡ በክሱ 3ኛ፣ 4ኛ፣ 6ኛ፣ 8ኛ፣11ኛ፣ 12ኛ እና 9ኛ ተራ ቁጥር ከተጠቀሰዉ ዞታ ዉስጥ 4 ቀርጥ በአጠቃላይ 26 ቀርጥ የዉርስ ይዞታ በመሆኑ አመልካች፣ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች እኩል ይካፈሉ በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝተዉ 1ኛ ተጠሪ፣ አመልካች እና የስር 4ኛ ጣልቃ ገብ በየበኩላቸዉ ባቀረቡት ቅሬተ መነሻነት ጉዳዩን የተመለከተዉ የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ መርምሮ አመልካች በክሱ 8ኛ፣ 11ኛ እና 12ኛ ተራ ቁጥር ያሉት ይዞታዎች የግላቸዉ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ የሌላቸዉ በመሆኑ ከዉርስ ዉጪ ይደረግልኝ በማለት ያቀረቡት ቅሬታ ተገቢነት የለዉም፡፡ የ1ኛ ተጠሪ አባት ከወላጆቹ ቀድሞ የሞተ ቢሆንም 1ኛ ተጠሪ በአባቱ ምትክ የአያቶቹን የዉርስ ይዞታ መዉረስ ይችላል፡፡ አመልካች በስጦታ ያገኘዉ ድርሻ ከአጠቃላይ ዉርሱ ክፍፍል ድርሻዉ በላይ የደረሰዉ በመሆኑ ከዉርሱ ሊካፈል አይገባም በማለት የወረዳዉን ፍ/ቤት ዉሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝቶ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርብም ግራ ቀኙን በመካከራከር ዉሳኔዉን አጽንቷል፡፡ በመቀጠል አመልካች ለክልሉ ሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን ችሎቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ ዉሳኔዉን በማጽናት ወስኗል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአመልካች ሰበር አቤቱታ ይዘት፡- በክሱ ተራ ቁጥር 11 እና 12ኛ ላይ የተጠቀሱት ይዞታዎች የሟቾች የነበሩ ቢሆንም አመልካች ከ1980 ዓ.ም ጀምሮ ከ30 ዓመት በላይ አመልካች በቁጥጥሬ ስር አድርጌ እየተጠቀምኩበት የገጠር የእርሻ መሬት የይዞታ ማረጋገጫ ያለኝ፤ ሟቾች በሕይወት በነበሩበት ጊዜ የይዞታ መብታቸዉን የተዉትን የዉርስ ይዞታ ነዉ በሚል ተጠሪዎች እንዲከፋፈሉት መወሰኑ ስህተት ነዉ፡፡ ለክስ ምክንያት ከሆኑ ይዞታዎች በክሱ ተራ ቁጥር 1፣ 2፣ 10፣ 9ኛ ላይ 5 ቀርጥ እንዲሁም 8፣ 11 እና 12ኛ ላይ ያሉትን ይዞታዎች በ1996 ዓ.ም ለገበሬ ሲለካ አመልካች ማረሚያ ቤት ስለነበርኩ ሟቾች ራሳቸዉ በይዞታዉ ላይ ቆመዉ በአመልካች ስም አስለክተዋል፡፡ ይህ ስለመሆኑም በወቅቱ መሬቱን ከለኩት ኮሚቴዎች ዉስጥ አቶ ደቻሳ ነገሪና አቶ ንጉሴ ደበላ በማስረጃነት ቀርበዉ በስር ፍ/ቤት አረጋግጠዋል፡፡ በተለይ በተራ ቁጥር 8ኛ ላይ የተጠቀሰዉ ይዞታ ባዶ መሬት የነበረና እንዲሰጠኝ ጠይቄ በግሌ ከመንግስት የተሰጠኝና ለ30 ዓመታት በቁጥጥር ስሬ አድርጌ ስጠቀምበት የነበረ እንጂ የሟቾች ይዞታ አልነበረም፡፡ ስለሆነም ሟቾች በሕይወት እያሉ የተዉትን ይዞታ ተጠሪዎች ይዞታዉን የሚወርሱበት አግባብ የለም፡፡ አመልካች የሟቾች የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ሆኖ ሳለ ከተጠሪዎች ጋር የዉርሱን ይዞታ ሊካፈል

አይገባም መባሉ ባልተጠየቀ ዳኝነት የተሰጠ በመሆኑ ስህተት ነዉ፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ በዚህ ረገድ ሊሻርና ተሻሽሎ ሊወሰን ይገባል የሚል ነዉ፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ በስር ፍ/ቤት ክርክር ከቀረበባቸዉ ይዞታዎች መካከል በክሱ ዝርዝር ተራ ቁጥር 8ኛ፣ 11ኛ እና 12ኛ ላይ የተጠቀሱትን ይዞታዎች አስመልክቶ የአሁኑ አመልካች በስማቸዉ የባለይዞታነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የወሰዱበት ስለመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ አረጋግጠዉ እያለ ይዞታዎቹ የዉርስ ሀብት ናቸዉ በሚል የወሰኑበት አግባብ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 40(4) እና ከክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 አንቀጽ 6(1)፣ 15(4) መሰረት ለአርሶ አደሮች ከተደረገዉ የባለይዞታነት መብት ጥበቃ አኳያ እንዲሁም የባለይዞታነትን በማወቅ በገጠር እርሻ መሬት ላይ የሚሰጥ የባለይዞታነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ከሚኖረዉ ዉጤት አንጻር ለመመርመር ሲባል መዝገቡ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል የተባለ ነዉ፡፡

1ኛ ተጠሪ በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎለት ባለመቅረቡ እንዲሁም 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በቀበሌ አስተዳደር በኩል በመኖሪያ ቤታቸዉ ላይ መጥሪያ ተለጥፎ ባለመቅረባቸዉ መልስ ለመስጠት እንዳልፈለጉ ተቆጥሮ መልስ የመስጠት መብታቸዉ ጥር 15 ቀን 2017 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ መታለፉን መዝገቡ ያሳያል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን እኛም አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡ የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር መርምረን እንደተረዳነዉ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሻዉ ጭብጥ፡- በክሱ ዝርዝር ተራ ቁጥር 8ኛ፣ 11ኛ እና 12ኛ ላይ የተጠቀሱትን ይዞታዎች አስመልክቶ የአሁኑ አመልካች በስማቸዉ የባለይዞታነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የወሰዱበት ስለመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ አረጋግጠዉ እያለ ይዞታዎቹ የዉርስ ሀብት ናቸዉ በሚል በስር ፍ/ቤቶች መወሰኑ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 40(4) እና ከክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 አንቀጽ 6(1)፣ 15(4) መሰረት ለአርሶ አደሮች ከተደረገዉ የባለይዞታነት መብት ጥበቃ አኳያ እንዲሁም የባለይዞታነትን በማወቅ በገጠር እርሻ መሬት ላይ የሚሰጥ የባለይዞታነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ከሚኖረዉ ዉጤት አንጻር ተገቢ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነዉ፡፡

አመልካች አጥብቀዉ እየተከራከሩ የሚገኙት በክሱ ተራ ቁጥር 8ኛ የተጠቀሰዉ ይዞታ ባዶ መሬት የነበረና እንዲሰጠዉ ጠይቆ ተፈቅዶለት ከ30 ዓመት በላይ ሲጠቀምበት የነበረ የግሉ ይዞታ መሆኑን እንዲሁም በ11ኛ እና 12ኛ ተራ ቁጥር የተገለጹት ይዞታዎች ቀደም ሲል የሚቸች የነበሩ ቢሆንም በጎጆ መዉጫነት ተሰጥቶት ከ30 ዓመት በላይ ሲጠቀምባቸዉ የነበሩና በስሙ ተመዝግበዉ የሚገኙ በመሆናቸዉ ከዉርስ ይዞታ ዉጪ ሊደረጉ ይገባል በሚል ነዉ፡፡ የስር ፍ/ቤቶች በተለይ የክልሉ ሰበር ችሎት በፍርዱ እንዳሰፈረዉ አሁን ክርክር ያስነሱ ይዞታዎች በአመልካች ስም ተመዝግበዉ እንደሚገኙና በምን ሁኔታ እንደተመዘገቡ ግልጽ እንዳልሆነ የሲናና ወረዳ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ለስር ፍ/ቤት ባቀረበዉ ሪፖርት አረጋግጧል፡፡ የክልሉ ሰበር ችሎት አሁን ክርክር ያስነሱት ይዞታዎች በአመልካች ስም ተመዝግቦ የሚገኙ መሆኑን ቢያረጋግጥም ይዞታዎች የዉርስ ይዞታ ናቸዉ በማለት ለሰጠዉ ዉሳኔ የሰጠዉ ምክንያት ይዞታዉ በአመልካች ስም መመዝገቡ ብቻ የባለይዞታነት መብት የሚያስገኘዉ አይደለም በሚል ነዉ፡፡ የዚህን ተገቢነት ቀጥለን እንመልከት፡፡

በሥር ፍ/ቤት ክርክሩ በተጀመረበት ወቅት ሥራ ላይ በነበረዉ የኦሮሚያ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 አንቀጽ 2(20 እና 21) እንዲሁም 15(4) አንድ የመሬት ይዞታ በስሙ ተመዝግቦ የይዞታ ማረጋገጫ የተሰጠዉ አርሶ አደር የገጠር መሬቱ ባለይዞታ እንደሆነ የሕግ ግምት እንደሚወሰድ የሚያስገነዝቡ ሲሆን ይህን አዋጅ የተካዉ አዋጅ ቁጥር 248/2015 አንቀጽ 2(37) ደግሞ “የባለ ይዞታነት ማረጋገጫ ማስረጃ ወይም ካርታ” ማለት የገጠር መሬት ባለይዞታነት እና የመጠቀም መብት ዋስትና ለማረጋገጥ በቢሮዉ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ሲሆን፤ በካርታዉ ላይ የተገለጸዉ የመሬት መጠን የምስክር ወረቀቱን የያዘዉ ሰዉ መሆኑን የሚያረጋግጥ በሌላ ማስረጃ ሊስተባበል የሚችል የሕግ ግምት የሚያስወስድ ማስረጃ ማለት እንደሆነ ትርጉም በመስጠት ደንግጓል፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለዉ ሌላ ጠንካራ ማስረጃ ካልቀረበና ካልተስተባበለ በስተቀር የገጠር መሬት በስሙ የተመዘገበ እና የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተሰጠዉ ሰዉ የገጠር መሬቱ ባለይዞታ እንደሆነ ስለሚቆጠር የሕግ ጥበቃ ሊደረግለት ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 40(4) መሰረት የገጠር መሬት ባለይዞታ የሆነ አርሶ አደር በሕግ አግባብ ካልሆነ በቀር ከመሬት ይዘታዉ ያለመነቀል ሕገ-መንግስታዊ ዋስትና ተሰጥቶታል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አሁን ክርክር ያስነሱትን በክሱ ዝርዝር ተራ ቁጥር 8ኛ፣ 11ኛ እና 12ኛ የተጠቀሱት የገጠር ይዞታዎች በአመልካች ስም ተመዝግበዉ መሆኑ ከሚመለከተዉ የሲናና ወረዳ

የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ተጣርቶ በቀረበዉ ሪፖርት ተረጋግጧል፡፡ አመልካች እነዚህን ይዞታዎች በእጁ አድርጎ እየተጠቀመ የሚገኝ መሆኑም ሆነ ምዝገባዉ የተከናወነዉ ወላጆቹ በሕይወት እያሉ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ ይዞታዎቹ ቀድሞ የሚኞች የነበሩ መሆናቸዉ ከዚህ ዓለም በሞት እስከተለዩበት ጊዜ ድረስ እየተጠቀሙበት እንደነበረ ወይም የባለይዞታነት መብታቸዉ ያልተቋረጠ መሆኑ እስካልተረጋገጠ ድረስ እንዲሁም በአመልካች ስም ተመዝግቦ የሚገኝ እና ለረጅም ጊዜ እየተጠቀመበት የሚገኝ መሆኑ ተረጋግጦ ባለበት ሁኔታ እነዚህ ይዞታዎች በምን አግባብ በአመልካች ስም እንደተመዘገቡ የሚገልጽ ነገር የለም በሚል የዉርስ ይዞታ ናቸዉ ሊባሉ አይገባም፡፡ አመልካች ክርክር ያስነሱ ይዞታዎችን ያለአግባብ በስሙ አስመዝግቦና ይዞ እየተገለገለበት ይገኛል ከተባለም ይዞታዎች የዉርስ አካል ናቸዉ ከመባሉ በፊት ይኸዉ ጥያቄ ቀርቦ ምዝገባዉ ሊሰረዝ ይገባል፡፡ ይህ ባልሆነበት ሁኔታ የገጠር መሬት ምዝገባና የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን ያለበቂ ምክንያት ዋጋ በማሳጣት ይዞታዎቹ የዉርስ ይዞታዎች ናቸዉ ብሎ መወሰን የአመልካችን በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 40(4) ጥበቃ የተደረገለትን ከገጠር መሬት ይዞታቸዉ ያለመነቀል መብታቸዉን የሚጥስ በመሆኑ ተገቢነት የለዉም፡፡ ስለሆነም በክሱ ተራ ቁጥር 8ኛ፣ 11ኛ እና 12ኛ የተጠቀሱት ይዘታዎች በአመልካች ስም ተመዝግበዉ የሚገኙ በመሆናቸዉ የአመልካች የግል ይዞታዎች ናቸዉ፡፡

ሲጠቃለል አሁን ክርክር ያስነሱት በክሱ ዝርዝር ተራ ቁጥር 8ኛ፣ 11ኛ እና 12ኛ የተጠቀሱት የመሬት ይዞታዎች በአመልካች ስም የተመዘገቡና ለረጅም ጊዜ በይዞታዉ ስር አድርጎ ሲጠቀምባቸዉ መቆየቱ በተረጋገጠበት ሁኔታ ቀድሞ የሚኞች ይዞታ ነበሩ በሚል መነሻ ብቻ የዉርስ ይዞታ ናቸዉ ተብሎ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠዉ ዉሳኔ የኦሮሚያ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 አንቀጽ 2(20 እና 21) እና 15(4) እንዲሁም የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 40(4) ድንጋጌዎችን ያላገናዘበ በፌዴራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሀ እና ለ) እና 10(1/ሐ) መሠረት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 33516 መጋቢት 14 ቀን 2014 ዓ.ም የሲናና ወረዳን ፍ/ቤት በማሻሻል ተሰጥቶ፣ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የደቡብ ምድብ ቋሚ ችሎት በመ/ቁ 381918 መስከረም 26 ቀን 2015 ዓ.ም በተሰጠ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 406964 የካቲት 21 ቀን 2015 ዓ.ም በተሰጠ ዉሳኔ የጸናዉ ዉሳኔ

በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1) መሠረት ተሻሽሏል፡፡

2. በክሱ ዝርዝር ተራ ቁጥር 8ኛ፣ 11ኛ እና 12ኛ የተጠቀሱት የገጠር መሬት ይዞታዎች የሟቾች የዉርስ ይዞታ አካል ናቸዉ ተብሎ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠዉ የዉሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡ የተጠቀሱት ይዞታዎች የአመልካች የግል ይዞታዎች ናቸዉ ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ሌላዉ የስር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 246233

የካቲት 26 ቀን 2017ዓ/ም

ዳኞች፡ ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ብርቅነሽ እሱባለው

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካቾች፡ 1. አፍሪካ ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ ጠበቃ ብርሃኑ ታደሰ ቀረቡ

2. የማነ ግርማይ ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ ጠበቃ ሀይሉ ንጋቱ ቀረቡ

ተጠሪ፡ የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ነ/ፈ ኤደን ጌታቸው ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ የቀረበው አመልካቾች የግልግል ዳኝነት ጉባኤ ግንቦት 15 ቀን 2014ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት በመዝገብ ቁጥር 230851 በ22/7/2015ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ ቅር በመሰኘት በ24/8/2015ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ተጠሪ ለግልግል ዳኝነት ጉባኤ በ1ኛ አመልካች ላይ ባቀረበው ክስ በተጠሪ እና በ2ኛ አመልካች(ስር ጣልቃገብ ) መካከል ከወራቤ እስከ በጆበር ያለውን 38.5ኪ..ሜ የመንገድ ስራ ፕሮጀክት ለማከናወን እ.ኤ.አ ሜይ 20 2016 ውል የተፈረመ ሲሆን የውሉም አይነት ስራ ተቋራጩ(2ኛ አመልካች) የዲዛይንና የግንባታ ስራውን በሙሉ በኃላፊነት የሚያከናውንበት ነው፡፡ በውሉ መሰረት ስራ ተቋራጩ የመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትና የማቅረብ ግዴታ ስላለበት ይህን ተከትሎ ተቋራጩ የውሉን 10% ይኀውም ለብር 45,844,565 እ.ኤ.አ ከሜይ 13 2016 ጀምሮ ለአራት አመት ጸንቶ የሚቆይ የቦንድ ፖሊሲ

ማስ ታወሻ፡ - ይህ የ ሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነ ድ ለ ጥና ትና ምር ምር ሥራ ወይምለ ግንዛቤ እ ን ጂ ለ ፍር ድ አ ፈ ጻ ጸ ምዓላ ማአ ያ ገ ለ ግል ም!

ቁጥሩ በተገለጸ 1ኛ አመልካች የመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትና ሰጥቷል፡፡ በውሉ መሰረት እ.ኤ.አ ጃንዋሪ 26 2017 የተጀመረው የግንባታ ስራ በ1095 ቀናት ተጠናቆ ለግዜያዊ ርክክብ ብቁ መደረግ ሲገባው እና ከአመት በኋላ ጃንዋሪ 2018 አፈጻጸሙ 30.38% መሆን ሲገባው የስራ ተቋራጩ አፈጻጸም የውሉ 8% ላይ ነበር፡፡ በዛን ግዜም ከውሉ መፈጸሚያ ግዜ 33.8% ባክኖ ነበር፡፡ ተጠሪ ለስራ ተቋራጩ በቂ የቅድሚያ ክፍያ ገንዘብ ቢሰጠውም፤ ሶስት የክፍያ ሰርተፍኬቶችም ጸድቀው ገንዘብ ቢከፈለውም፤ የውል ግዴታውን እንዲወጣ ተጠሪና የፕሮጀክቱ አማካሪ ድርጅት ተደጋጋሚ ማሳሰቢያና ማስጠንቀቂያ ቢሰጡትም ይህን ባለመቀበል የግንባታ ቦታውን ጥሎ በመሄድ አይነተኛና መሰረታዊ የውል ጥሰት በመፈጸሙ ተጠሪ በውሉ መሰረት እ.ኤ.አ በ1/3/18 በተጻፈ ደብዳቤ የ2ኛ አመልካችን(ስራ ተቋራጭ) የስራ ውል አቋርጧል፡፡

የስራ ውል መቋረጡን ተከትሎ 1ኛ አመልካች የዋስትናውን ገንዘብ ገቢ እንዲያደርግ ተጠሪ ቢጠይቀውም የተለያዩ ምክንያቶችን በማቅረብ የዋስትና ግዴታውን ለመወጣት ፈቃደኛ ባለመሆኑ 1ኛ አመልካች በመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትና መሰረት ብር 45,844,565 ክፍያ እንዲፈጽም ከተጠየቀበት ግዜ ከ27/6/2010ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍል እንዲወሰንበት በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡ የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎችንም አቅርቧል፡፡

1ኛ አመልካች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን አቅርቦ በፍሬጉዳዩ ላይ ኃላፊነትን በተመለከተ ባቀረበው መልስ 2ኛ አመልካች ወደ ክርክሩ እንዲገባ ጠይቆ የዋናው ባለእዳ( ስራ ተቋራጩ 2ኛ አመልካች) ኃላፊነት ሳይረጋገጥ የ1ኛ አመልካች(ዋስ) ኃላፊነት ሊኖር አይችልም፤ 2ኛ አመልካች እንደውሉ ለመፈጸም ያልቻለው ከአቅም በላይ የሆነ ድንገተኛ ችግር ስላጋጠመው ሲሆን አመልካቾች ውሉ እንዳይቋረጥ ተገቢውን ጥረት አድርገዋል፡፡ እንደውሉ እንዳይፈጸም ምክንያት የሆነው ተጠሪ ነው፤ ውሉ ከተቋረጠም በኋላም አመልካቾች ስራው ከቆመበት እንዲቀጥልና እንደውሉ እንዲፈጸም ጥረት ቢያደርጉም ተጠሪ የአመልካቾችን ምክረ ሀሳቦች ውድቅ በማድረግ ለኪሳራው መጨመር ኃላፊ ነው፡፡ በዋስትና ሰነዱ በተቀመጠው ቅድመ ሁኔታ መሰረት ተጠሪ ክሱን በ12 ወራት ግዜ ውስጥ ማቅረብ ሲገባው ቀነ ገደቡን ተላልፎ በማቅረቡ ከቦንዱ ቅድመ ሁኔታዎች ተጠቃሚ ሊሆን አይችልም፡፡ ስለሆነም ክሱ ውድቅ እንዲደረግ፡፡ ይህ ታልፎ አመልካቾች በኃላፊነት የሚጠየቁበት አግባብ ቢኖር የኃላፊነት መጠንን በተመለከተ በዋናው ውል እና በልዩ ሁኔታዎች ድንጋጌዎች መሰረት የጉዳት ካሳ ወሰን የኮንትራት ዋጋው 10% ሆኖ የተረጋገጠው የጉዳት ካሳ መጠን የሚወሰደው ደግሞ የተከናወነው እለታዊ የስራ ዋጋ ተቀንሶለት መሆን ሲገባው ተጠሪ በዋስትና ሰነዱ ላይ እስከ ብር 45,844,565.00 በተባለው ላይ ምንም የሂሳብ ማቀናነሻ ሳይደረግ የሀላፊነቱን ጣሪያ መጠየቁ ተገቢ አይደለም እንዲባል እና ሂሳቡ በባለሙያዎች እንዲጣራ እንዲታዘዝ፤ በግንባታው ሳይት ላይ የነበሩ የ2ኛ አመልካች ንብረቶች ተጠሪ እና 2ኛ አመልካች በሚያቋቁሙት የጋራ ሂሳብ አጣሪዎች ተመርምሮ ተገቢው የሂሳብ መግለጫ ለጉባኤው እንዲቀርብ እንዲታዘዝልን በማለት ተከራክሯል፡፡ የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎችንም አቅርቧል፡፡ 2ኛ አመልካች ወደ ክርክሩ በጣልቃገብነት ገብቶ የመጀመሪያ ደረጃ

መቃወሚያዎችን አቅርቦ ፍሬጉዳዩን በተመለከተም 1ኛ አመልካች በፍሬጉዳዩ ላይ ካቀረበው መልስ ጋር ተመሳሳይ ይዘት ያለውን ክርክር አቅርቧል፡፡

የግልግል ዳኝነት ጉባኤውም የአመልካቾችን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች በብይን ውድቅ አድርጎ ፍሬጉዳዩን በተመለከተም ጭብጦችን በመያዝ ከቀረቡ ማስረጃዎች ጋር ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ 1ኛ አመልካች በገባው የዋስትና ውል መሰረት ብር 45,844,565 ከነወለዱ እንዲከፈል በማለት ያቀረበውን የዳኝነት ጥያቄ በተመለከተ ስራ ተቋራጩ 2ኛ አመልካች የውል ግዴታውን መወጣት ያልቻለው ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ስለገጠመው ነው በማለት አመልካቾች ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፤ 2ኛ አመልካች የውል ግዴታውን በአግባቡ ሊወጣ አልቻለም፡፡ በዋስትና ውሉ እና በግንባታ ውሉ መሰረት ተጠሪ ለ1ኛ አመልካች ተገቢውን ቅድመ ማስጠንቀቂያና ማስጠንቀቂያ ሰጥቷል፡፡ 1ኛ አመልካች በሰጠው ዋስትና መሰረት ካሳ እንዲከፍል ሲጠየቅ ስራ ተቋራጩ ያልተወጣውን ግዴታ 1ኛ አመልካች በመረጠው ሌላ ስራ ተቋራጭ በተክለብርሃን አምባዬ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር አማካኝነት ተወጥቶ ፕሮጀክቱን ከዳር ለማድረስ ለተጠሪ በደብዳቤ በጠየቀው መሰረት 1ኛ አመልካች በመረጠው ተቋራጭ ስራው እንዲቀጥል ፈቃደኛነቱን ለ1ኛ አመልካች በደብዳቤ ቢገልጽም 1ኛ አመልካች ዝርዝር እቅድ በማቅረብ ግዴታውን ለመወጣት አልቻለም፡፡ ስለሆነም 2ኛ አመልካች(ስራ ተቋራጩ) ከውሉ አፈጻጸም ረገድ በተግባር ካሳየው ሁኔታ በመነሳት 1ኛ አመልካች ለተጠሪ በሰጠው ዋስትና መሰረት የዋስትና ገንዘቡን ብር 45,844,565.00(አርባ አምስት ሚሊዮን ስምንት መቶ አርባ አራት ሺህ አምስት መቶ ስልሳ አምስት ብር) ከ26/7/2010ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ሌሎች ጭብጦችም ላይ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካቾች ይግባኝ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት አቅርበው ፍርድቤቱም በሰጠው ትእዛዝ ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ከላይ የተገለጹትን ውሳኔ እና ብይን በመቃወም ሲሆን ይዘቱም የዋስትና ውሉ የአንድነትና የነጠላ ኃላፊነት በሆነበት እና 2ኛ አመልካች በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 41 መሰረት ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር ተፈቅዶለት እስከ መጨረሻው የክርክር ሂደት ድረስ ተካፋይ በሆነበት ጉባኤው የ2ኛ አመልካችን ኃላፊነት በተመለከተ ምንም አይነት ውሳኔ ሳይሰጥ በዝምታ ማለፉም ሆነ የይግባኝ ሰሚ ፍርድቤትን ይህንኑ ትእዛዝ ማጽናቱ፤ በህግና በውል መሰረት የዋናው ባለእዳ(2ኛ አመልካች) ኃላፊነት ሳይረጋገጥ ዋሱ(1ኛ አመልካች) ኃላፊ ነው ተብሎ መወሰኑ፤ ለውሉ አፈጻጸም መዘግየት ተጠሪ ተጠያቂ ነው ተብሎ አለመወሰኑ፤ 2ኛ አመልካች የውል ግዴታውን እየተወጣ ሳለ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ አጋጥሞት ነበር በማለት ያስረዳው እና በበቂ ማስረጃ ያረጋገጥነው መታለፉ፤ 2ኛ አመልካች ካጋጠመው ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ለመውጣት ለተጠሪ ያቀረበው የግዜያዊ የገንዘብ ድጋፍና የግዜ ማራዘሚያ ጥያቄዎች አለአግባብ በተጠሪ መታለፋቸው እና ይህም በስር ጉባኤ እና በይግባኝ ሰሚ ፍርድቤት ሳይታይ መታለፉ፤ ተጠሪ ክስ ያቀረበው በቦንዱ ላይ ቅድመ ሁኔታ ሆኖ የተቀመጠውን( condition precedent) በመተላለፍ ስለሆነ 1ኛ አመልካች ከኃላፊነት ነጻ ነው ተብሎ አለመወሰኑ፤ ለጉዳት ኪሳራው መጨመር

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

ኃላፊው ተጠሪ ነው ተብሎ አለመወሰኑ፣ ተጠሪ የጠየቀው የጉዳት ካሳ መጠን የህጉን እና የውሉን ድንጋጌዎች ያልተከተለ በሆነበት የስር ጉባኤ የካሳውን ጥያቄ እንዳለ መቀበሉ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት በመሆናቸው የግልግል ዳኝነት ጉባኤም ሆነ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ እና ትእዛዝ እንዲሻር፣ ይህ ከታለፈ የኃላፊነት መጠንን አስመልክቶ 1ኛ አመልካች ያቀረበው እንዲታይ ተገቢው ጭብጥ ተይዞ መዝገቡ ወደ ስር ጉባኤ እንዲመለስ እንዲወሰንልን፣ ወጪና ኪሳራ እንዲከፈለን እንዲወሰንልን የሚል ነው፡፡

ይህ አቤቱታቸው ተመርምሮ የግንባታ ስራ መዘግየቱን በተመለከተ 2ኛ አመልካች ያቀረባቸው ምክንያቶች የታለፉበት አግባብነት፣ የመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትና በተመለከተ ኃላፊነት ላይ 2ኛ አመልካች በዝምታ የታለፈበትን አግባብነት፣ የዋስትና ውሉ በሁኔታ ላይ የተመሰረተ መሆን አለመሆኑን እና ሁኔታዎቹ የተሟሉ መሆን አለመሆኑ(የሰ.መ.ቁ 218338 እና ሌሎች ይመለከታል) እንዲሁም ሌሎች የአቤቱታ ነጥቦችን በግራቀኙ መካከል የተደረገውን ውል እና አግባብነት ያለውን ህግ ያገናዘበ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ተጠሪን ያስቀርባል በማለት በ28/11/2015ዓ.ም በተሰጠው ትእዛዝ መሰረት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጓል፡፡ ተጠሪ በ14/3/2016ዓ.ም በተጻፈ ባቀረበው መልስ የግልግል ዳኝነት ጉባኤውም ሆነ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ እና ትእዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አልተፈጸመበትም የሚልበትን ምክንያቶች በመዘርዘር እንዲጸና፣ ወጪና ኪሳራ እንዲከፈለው እንዲወሰን ጠይቋል፡፡ አመልካቾች በ2/4/2016ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታውን፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ትእዛዝ እንዲሁም ከተገቢዎቹ የህግ ድንጋጌዎች አንጻር የግልግል ዳኝነት ጉባኤ እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ እና ትእዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸውን የመጨረሻ ውሳኔዎች ማረም ስለመሆኑ በኢፌዲሪ ህገመንግስት አንቀጽ 80(3)(ለ) እንዲሁም በፌደራል ፍርድቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4) እና 10(1) በተዘረዘሩት ድንጋጌዎች ተቀምጧል፡፡ በሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ሊባል የሚችለው በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለዉ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን፣ ህግ ያላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉን ህግ የሚጠቅስ፣ ለክርክሩ አግባብነት ያለዉ ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለዉ ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፣ በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ዉድቅ በማድረግ የተወሰነ፣ በፍርድ አፈፃፀም ሂደት ከዋናዉ ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትዕዛዝ የተሰጠበት፣ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት

ስልጣን ሳይኖር የተወሰነ፣ የአስተዳደር አካል ወይም ተቋም ከህግ ዉጭ የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ በመቃረን የተወሰነ ሲሆን ነዉ፡፡

በያዝነው ጉዳይ የግልግል ዳኝነት ጉባኤ 1ኛ አመልካች ለተጠሪ የሰጠው የመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትና ሰነድ " ያለፉት ሁኔታዎች እና ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ስራ ተቋራጩ የውሉን ሁሉንም ዝርዝሮች ሁኔታዎች እና ቃልኪዳኖች ማክበር ሲኖርበት ስራ ተቋራጩ ውል ከጣሰ ዋሱ የደረሰውን ጉዳት ለማስተካከል ለአሰሪው የውሉን ዋጋ እስከ 10% የኢትዮጵያ ብር 45,844,565.(አርባ አምስት ሚሊዮን ስምንት መቶ አርባ አራት ሺህ አምስት መቶ ስልሳ አምስት ብር) ከፍሎ ይህ ግዴታ የተሻረ እና ቀሪ ይሆናል፤ ያለበለዚያ ውሉ ከተፈጸመበት እ.ኤ.አ ከሜይ 20 ቀን 2016 ጀምሮ ለአራት አመት ከአንድ ወር ጸንቶ መቆየት አለበት " የሚል ይዘት ያለው መሆኑን፤ በዚህ የዋስትና ውሉ ድንጋጌ መሰረት 1ኛ አመልካች የዋስትና ገንዘቡን ለተጠሪ የሚከፍለው የደረሰውን ጉዳት ለማስተካከል መሆኑን፤ የዋስትና ገንዘቡ እንዲከፈል በተጠሪ ላይ የደረሰ ጉዳት መኖሩ አስፈላጊ መሆኑን እና ከዚህ አንጻርም ስራ ተቋራጩ 2ኛ አመልካች የውል ግዴታውን ባለመወጣቱ በተጠሪ ላይ ከፍተኛ ጉዳት የደረሰበት መሆኑን በፍሬነገር ደረጃ በማረጋገጥ፤ አመልካቾች የውል ግዴታውን ለመወጣት ያልቻልነው ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ነው በማለት ያቀረቡትን የፍሬነገር ክርክር መርምሮ ውድቅ በማድረግ፤ እንዲሁም 1ኛ አመልካች በሰጠው ዋስትና መሰረት ካሳ እንዲከፍል ሲጠየቅ ስራ ተቋራጩ ያልተወጣውን ግዴታ 1ኛ አመልካች በመረጠው ሌላ ስራ ተቋራጭ በተክለብርሃን አምባዬ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር አማካኝነት ተወጥቶ ፕሮጀክቱን ከዳር ለማድረስ ለተጠሪ በደብዳቤ በጠየቀው መሰረት 1ኛ አመልካች በመረጠው ተቋራጭ ስራው እንዲቀጥል ፈቃደኛነቱን ለ1ኛ አመልካች በደብዳቤ ቢገልጽም 1ኛ አመልካች ዝርዝር እቅድ በማቅረብ ግዴታውን ለመወጣት አለመቻሉን በማረጋገጥ 1ኛ አመልካች ለተጠሪ በሰጠው ዋስትና መሰረት የዋስትና ገንዘቡን ብር 45,844,565 (አርባ አምስት ሚሊዮን ስምንት መቶ አርባ አራት ሺህ አምስት መቶ ስልሳ አምስት ብር) ከ26/7/2010ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል በማለት የሰጠው ውሳኔም ሆነ በዚህ ውሳኔ ላይ የቀረበውን ይግባኝ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመሰረዝ የሰጠውን ትእዛዝ ይህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘውም፡፡

አመልካቾች በሰበር አቤቱታቸው የዋስትና ውሉ የአንድነትና የነጠላ ኃላፊነት በሆነበት እና 2ኛ አመልካች በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 41 መሰረት ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር ተፈቅዶለት እስከ መጨረሻው የክርክር ሂደት ድረስ ተካፋይ በሆነበት ጉባኤው የ2ኛ አመልካችን ኃላፊነት በተመለከተ ምንም አይነት ውሳኔ ሳይሰጥ በዝምታ ማለፉም ሆነ የይግባኝ ሰሚ ፍርድቤት ይህንኑ ትእዛዝ ማጽናቱ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ነው በማለት ያቀረቡትን ቅሬታ በተመለከተ አመልካቾች አንዳቸው ለአንዳቸው ያለባቸውን ኃላፊነት እርስ በራሳቸው ከሚጠያየቁ በቀር 2ኛ አመልካች በጣልቃገብነት በክርክሩ ተካፋይ ከሆነ በኋላ ኃላፊነቱን በተመለከተ የግልግል ዳኝነት ጉባኤው ለምን በዝምታ አለፈ በማለት ሊጠይቁ የሚችሉበት የህግ አግባብ ባለመኖሩ በዚህ ረገድ የቀረበውን የሰበር አቤቱታ ይህ ችሎት አልተቀበለውም፡፡ ስለሆነም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. የግልግል ዳኝነት ጉባኤ ግንቦት 15 ቀን 2014ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት በመዝገብ ቁጥር 230851 በ22/7/2015ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ጸንተዋል፡፡
2. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ጉዳዩን አይቶ ለወሰነው ለግልግል ዳኝነት ጉባኤ እና ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት ይድረሳቸው፡፡
3. በዚህ መዝገብ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት በኮ.መ.ቁ 301054 የተጀመረው አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ በ11/9/2015ዓ.ም የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
4. መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 247702

የካቲት 28 ቀን 2017ዓ/ም

ዳኞች ፡- ገበየሁ ፈለቀ

አለማየሁ ሹናራ

ደረጀ አያና

ኑረዲን ከድር

ብርሃኑ መንግሥቱ

አመልካች፡- 1ኛ አቶ ግርማ አዳነ
2ኛ አቶ ደሳለኝ አምሃ } ጠበቃ ሲሳይ ወልዴ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ላልይበላ ንግድ ስራዎች ኃ/የተ/የግ/ማህበር:- የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ አላግባብ ከማህበር የተሰናበትን በመሆኑ እንዲንመለስ ወይም ከማህበሩ ያለን ድርሻችን እንዲከፈለን በሚል የቀረበ ክስ ይርጋን የሚመለከት ነው፡፡ክርክሩ የተጀመረዉ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሲሆን አመልካቾች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡አመልካቾች በተጠሪ እና 2ኛ ተከሳሽ በነበሩት በአቶ ጌታቸው ፈጠነ ላይ ባቀረቡት ክስ የቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ በላልይበላ ከተማ በንግድ ማህበር ተደራጅተን እየሰራን በሂደት 19 ክፍል የያዘ ሆቴል ገንብተን በለልይበላ ነጋዴዎች ማህበር ስም እየሰራን እያለ በአክሲዮን ሽያጭ ጠቅላላ ካፒታላችን ብር 2,295,500(ሁለት ሚሊዮን ሁለት መቶ ዘጠና አምስት ሺ አምስት መቶ ብር) ስለደረሰ በ2002 ዓ.ም የማህበሩ ገንዘብ ያዥ የነበሩ የማህበሩ ስራ አስኪያጅ የሆነው ሁለተኛ ተከሳሽ የ10 ሰዎችን አክሲዮን ገዝቻለው በሚል ከ10 ሰዎች ውጪ ባለነው በ21 አባላት ስም እንደ አዲስ

ማህበር መመስረት አለብን በማለት ለማህበሩ ሀሳብ አቅርቦ ከሰኔ 22 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ የማህበሩ ስም ወደ ጌታቸው ግርማ እና ጓደኞቹ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በሚል ቀይሮ እየሰራ እያለ በማህበሩ አካላት መካከል አለመግባባት ተፈጥሮአል፡፡አመልካቾች እንደ ቁጥጥር ኮሚቴ አባልነታችን በመመስረቻ ፅሁፍ አንቀፅ 8 በተሰጠን ስልጣን መሰረት የአመራር ግድፈቶች እንዲስተካከሉ የምናደርገውን ቁጥጥር በመቃወም የመተዳደሪያ ደንቡ አንቀፅ 4(2) ባላገናዘበ መልኩ አለአግባብ ከማህበሩ ስላሰናበተን ወደ ማህበራችን እንድንመለስ፣ወደ ማህበሩ የማንመለስ ከሆነም ንብረቱ ተጣርቶ በአዲስ መልክ ከተመሰረተበት ከ1997 ጀምሮ ማህበሩ ኦዲት ተደርጎ ጉዳዩ የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚሰጥበት የሚገኘው ድርሻችን እና ትርፋችን ታስቦ እንዲከፈለን የሚል ነው፡፡ተጠሪም በሰጡት መልስ በአመልካቾች የቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ይሆናል የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ፍ/ቤቱም ይርጋን በተመለከተ የቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በፍ/ህ/ቁጥር 448(2) መሰረት በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ላይ የሚቀርብ እንጂ ለማህበር ይፍረስልን እና ድርሻችን ይሰጠን ጥያቄ ላይ የሚቀርብ ስላልሆነ እንዲሁም ግንኙነታቸው በአንድ ጊዜ የሚጠናቀቅ ባለመሆኑ የይርጋውን መቃወሚያውን ውድቅ በማድረግ በፍሬ ነገሩ ላይ የግራ ቀኙን ማስረጃ መዝኖ የአመልካቾች ስንብት ህገ-ወጥ ስለሆነ ወደ ማህበሩ እንዲመለሱ እና ድርሻቸው ተካቶ የተሰራው የአክሲዮን ድልድል ታርሞ ክፍፍሉ ይፈፀም ሲል ወስኗል፡፡

ተጠሪም በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታቸውን ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም በሰጠው ውሳኔ በንግድ ህግ ቁጥር 416(2)(3) መሰረት አመልካቾች የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔውን መስጠቱን ባወቁበት ወይም በንግድ መዝገብ በተመዘገበበት በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ክስ ካልቀረበ ጥያቄው ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ ይደነግጋል፣አመልካቾች ክስ ያቀረቡት ማህበሩ በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ከሰጠ ከአንድ አመት ከስድት ወር በላይ ቆይተው በመሆኑ የስር ፍ/ቤት የአመልካቾች ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ሆኖ ሳለ በይርጋ አይቋረጥም በማለት የሰጠው ብይን ተገቢነት የለውም በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር አመልካቾች ወደ ማህበሩ ለመመለስ ያቀረቡት ክስ በይርጋ የተቋረጠ በመሆኑ ወደ ማህበሩ ሊመለሱ አይገባም የሚል ውሳኔ ሰጥቷል ፡፡

አመልካቾች ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በግንቦት 18 ቀን 2015 ዓ.ም ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በሚል መነሻነት ነው፡፡በአመልካቾች የቀረበው የሰበር አቤቱታ ይዘትም በአጭሩ ተጠሪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሆኖ እያለ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ለአክሲዮን ማህበር የተደነገገውን የንግድ ሕግ ቁጥር 416(2) በመጥቀስ አመልካቾች ወደ ማህበሩ እንድንመለስ ይወሰንልን በማለት ያቀረብነውን ዳኝነት በይርጋ ቀሪ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ አግባብነት የሌለውን ሕግ በመጥቀስ በመሆኑ ተገቢ አይደለም፣አክሲዮን ማህበርን የሚመለከተው

የሕግ ድንጋጌ ለኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር አግባብነት የለውም የሚለው መከራከሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብነት አለው ቢባል እንኳን አመልካቾች በግላችን ከማህበር እንድንሰናበት በተሰጠው ውሳኔ ላይ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል የሕግ ድንጋጌ ባለመሆኑ ተጠሪ አመልካቾችን ከአባልነት እንዲሰናበቱ የሰጠውን ውሳኔ በንግድ ሕጉ ቁጥር 416 (2) እንደሚሸፈን አድርጎ በይርጋ ይታገዳል ሲል የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፀመበት ነው፡፡ተጠሪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በመሆኑ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ጠቅላላ ጉባዔ በማህበርተኛ ላይ የሚሰጡትን ግላዊ የሆኑ ውሳኔዎች በተመለከተ ለፍ/ቤት ክስ የማቅረቢያ ጊዜ ወይም የይርጋ ድንጋጌ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 7 ከቁጥር 510 ጀምሮ ባሉት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በሚመራበት የሕግ ድንጋጌ ውስጥ የተደነገገ ባለመሆኑ በልዩ ሕጉ የተቀመጠ የይርጋ ድንጋጌ ከሌለ በፍ/ብሔር ሕግ ቁጥር 1845 የተደነገገው ጠቅላላ የይርጋ ድንጋጌ ተፈፃሚ ሊሆን እንደሚገባ በሰበር ሰሚ ችሎት አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የተሰጠበት ነው፡፡ስለሆነም ያቀረብነው ክስ በአስር ዓመት የይርጋ ድንጋጌ የሚታይ ሆኖ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ አቤቱታው አልቀረበም በማለት በይርጋ ቀሪ እንደሆነ ተድርጎ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ እንዲታረምልን የሚል ነው፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም አመልካቾች ከጠየቁት ዳኝነት አንፃር ያቀረቡት ክስ በንግድ ህጉ አንቀፅ 416(2) ስር በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ስላልቀረበ በይርጋ ቀሪ ነው የመባሉን አግባብነት ከድንጋጌው እንዲሁም በሰበር መዝገብ ቁጥር 230139 እና 163547 ከተሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ አንፃር የውሳኔውን ተገቢነት ለማጣራት ሲባል ተጠሪ መልስ እንዲሰጡ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡

ተጠሪም በቀረበው የሰበር አቤቱታ ላይ የካቲት 18 ቀን 2016 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡በተጠሪ የቀረበውም መልስ አጠር ባለ መልኩ ከማህበር ጋር የሚገናኙ ማንኛዉም ክርክሮች ሊገዙ የሚገባቸዉ በማኅበሩ መመስረቻ ጽሁፍ እና የማህበሩ የዉስጥ መተዳደሪያ ደንብ ላይ በግልጽ በተቀመጡ ድንጋጌዎች ሲሆን የተፈጠረዉ ጉዳይ በእነዚህ የማህበሩ ሰነዶች የማይሸፈን ከሆነ ለጉዳዩ አግባብነት ያለዉ የንግድ ህግ እና የፍ/ብሄር ህግ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡በተጠሪ ማህበር መመስረቻ ጽሁፍ እና በማህበሩ የዉስጥ መተዳደሪያ ደንብ በማይሸፈኑ ጉዳዮች አግባብነት ያለዉ የንግድ ህግ እና የፍ/ብሄር ህግ ተፈጻሚ እንደሚሆን በግልጽ ተመላክቷል፡፡ከፍ/ብሄር ህግ ድንጋጌዎች ዉስጥ አሁን ለተያዘዉ ጉዳይ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845 የተመለከተዉ ጠቅላላ የይርጋ ደንብ ሳይሆን ስለማህበሮች የተመለከተዉ ልዩ የይርጋ ደንብ የፍ/ብ/ህ/ቁ.424(3) አግባብነት ይኖረዋል፡፡በመሆኑም አመልካቾች ከማህበሩ የተሰናበቱ መሆኑን ባወቁ በሶስት ወር ጊዜ ዉስጥ ስልጣን ላለዉ ፍ/ቤት ክስ አቅርበናል በሚል ያልተከራከሩ በመሆኑ እና ክስ የማቅረብ መብታቸዉ ይርጋ ቀሪ ሊሆን ስለሚገባ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በአመልካቾች እና በተጠሪ ማህበር መካከል ያለዉ ክርክር መቅረብ የሚገባዉ በምን ያህል ጊዜ ነዉ የሚለዉን የሚሸፍን የይርጋ ድንጋጌ በሚመለከት የንግድ ህግ.ቁ.416 ቢጠቅስም ከዉሳኔዉ ጠቅላላ

ይዘት እና ከይርጋ ደንቦች አጠቃላይ አላማ እና መርህ አንጻር ሲታይ ክሱ በፍ/ብ/ህ/ቁ.424(3) መሰረት በ3 ወር ይርጋ ቀሪ ስለሚሆን የተሰጠዉ ዉሳኔ የድንጋጌ ለዉጥ ቢደረግበትም በዉጤት ደረጃ ለዉጥ የማያመጣ በመሆኑ በፌ/ጠ/ፍ/ቤት የተሰጠዉ ዉሳኔ ሊጸና ይገባል በሚል ተከራክረዋል፡፡

አመልካቾችም በመጋቢት 10 ቀን 2016 ዓ.ም የተሰጠ የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለጸውን የሚመስል ሲሆን ችሎቱ የያዘዉን ጭብጥ ከግምት ውስጥ በማስገባት በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል መሰረታዊ የሕግ ስህተት መፈጸም አለመፈጸሙን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነዉም በቅድሚያ ይህ ችሎት በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት በተ.ቁ ሶስት ላይ ከተሰየሙት ዳኛ አሿሿም ጋር በተገናኘ የያዘው ተጨማሪ ጭብጥ ሥነ ሥርዓታዊ ጉዳዩን የሚመለከት በመሆኑ በቅድሚያ መታየት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ይህ ችሎት በሰ.መ.ቁ 250725 ከዳኞች አሿሿምን በሚመለከት በአብላጫ ድምጽ ተሰጥቶ የነበረውን የሕግ ትርጉም መሠረት በማድረግ በዚህ መዝገብ ላይ ተጨማሪ ጭብጥ ይዞ የነበረ ቢሆንም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰባት ዳኞች በተሰየሙበት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰመ.ቁ 242695 ጥቅምት 04 ቀን 2017 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ በሰ.መ.ቁ 250725 የተሰጠው የሕግ ትርጉም ተለውጦ በአዋጅ 1233/2013 አንቀጽ 26(2) መሰረት በዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የተሰጠው ውሳኔ ዳኞችን በጊዜያዊነት ከአንድ ደረጃ ፍርድ ቤት ወደሌላ ደረጃ ፍርድ ቤት አዛውሮ ማሰራት እንጂ የዳኝነት ሹመት ባለመሆኑ እና በሕግ አውጪው በወጣና ጸንቶ ባለ ሕግ በተሰጠ ስልጣን መሰረት የተከናወነ ሕጋዊ ተግባር በመሆኑ በዝውውር በጊዜያዊነት የተመደቡ ዳኛ በተሰየሙበት ችሎት የተሰጠው ውሳኔ ባልተሟላ ዳኛ የተሰጠ ውሳኔ ነው ሊባል አይችልም በሚል ችሎቱ አስቀድሞ ሰጥቶት የነበረውን  የሕግ ትርጉም በሰባት ዳኛ የተለወጠ በመሆኑ በዚህ ረገድ በዚህ ችሎት የተያዘው ተጨማሪ ጭብጥ ቀሪ ሆኗል፡፡ስለሆነም ዋናውን ጉዳይ በሚመለከት በዚህ ችሎት አስቀድሞ የተያዘውን ጭብጥ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አሁን የቀረበውን ክርክር በሚመለከት አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ የመተዳደሪያ ደንቡን ባላገናዘበ መልኩ አለአግባብ ከማህበሩ ስለተሰናበተን ወደ ማህበራችን እንድንመለስ፣ወደ ማህበሩ የማንመለስ ከሆነም ንብረቱ ተጣርቶ በአዲስ መልክ ከተመሰረተበት ከ1997 ጀምሮ ኦዲት ተደርጎ ጉዳዩ የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚሰጥበት የሚገኘው ድርሻችን እና ትርፋችን ታስቦ እንዲከፈለን የሚል ሲሆን ተጠሪም  በሰጡት መልስ አመልካቾች በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ከማህበሩ እንዲሰናበቱ ውሳኔ በተላለፈ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ውሳኔው እንዲሻር ለፍ/ቤት ክስ ያላቀረቡ ስለሆነ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሊሆን ይገባል በሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና በፍሬ ነገር ላይም መልስ ሰጥተዋል፡፡ ክሱ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩ በይርጋ የሚቋረጥ አይደለም

በሚል በፍሬ ነገር ላይ ውሳኔ ያሳረፈ ሲሆን የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ጉዳዩን በይግባኝ በማየት አመልካቾች ወደ ማህበሩ እንዲመለሱ በሚል ያቀረቡት ክስ በንግድ ህግ ቁጥር 416(2) መሠረት በይርጋ ቀሪ ሊሆን ይገባል በሚል የወሰነ ስለመሆኑ የሚያስገነዝብ ነው፡፡

ከላይ እንደተመለከተው አመልካቾች የመብት ጥያቄ በማቅረባችን ከማህበሩ የተሰናበትን በመሆኑ መብታችን እንዲከበር በሚል ባቀረቡት አቤቱታ ላይ የቀድሞው የንግድ ህግ አንቀጽ 416(2) ላይ የተጠቀሰው የይርጋ ድንጋጌ ለጉዳዩ ያለውን የተፈፃሚነት ወሰን መለየቱ አስፈላጊ ነው፡፡የቀድሞ የንግድ ህግ አንቀጽ 416(2) ህግን፣የማህበሩን መመስረቻ ጽሑፍና የመተዳደሪያ ደንብን ባለመከተል የተደረጉትን ውሳኔዎች ውሳኔው ከተሰጠበት ጊዜ አንስቶ በሶስት ወር ውስጥ ወይም በንግድ መዝገብ ተመዝግቦ እንደሆነም ከተመዘገበበት ቀን አንስቶ በሶስት ወር ውስጥ ማንኛውም ባለጥቅም ሊቃወማቸው የሚችል ስለመሆኑ የሚደነግግ ሲሆን ህግን፣የማህበሩን መመስረቻ ጽሑፍና የመተዳደሪያ ደንብን በመከተል የተደረጉ የጉባኤው ውሳኔዎች በጉባኤው ያልተገኙትን ወይም በሃሳብ ያልተስማሙትን ማህበርተኞችን ሁሉ ሊያስገድድ የሚችል ስለመሆኑ በህጉ ድንጋጌ አንቀጽ 416(1) ስር ተመልክቷል፡፡ከዚህ የንግድ ህግ አንቀጽ 416(2) ይዘት መረዳት የሚቻለው የማህበሩን ቃለ ጉባኤ ለመቃወም በጉባኤው የተላለፈው ውሳኔ ህግን፣የማህበሩን መመስረቻ ጽሑፍ እንደዚሁም የመተዳደሪያ ደንቡን በመተላለፍ የተሰጠ ሆኖ ሲገኝ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡የማህበሩን ቃለ ጉባኤ ለመቃወም የሚቻለው በአንድ በኩል ህግን በመፃረር ውሳኔ ሲሰጥ ሲሆን በሌላም በኩል ደግሞ የህግ ወይም የመመስረቻ ጽሑፍ ጥሰቱ ከጉባኤው አጠራር ጋር ወይም አካሄድ በመጣስ የሚፈጸም ስለመሆኑ መመልከት የሚቻል ቢሆንም በንግድ ህጉ በግልጽ ተደንግጎ የሚገኝ አይደለም፡፡በዚህ መሠረት የንግድ ህግ አንቀጽ 416(2) ሲታይ የጉባኤውን አጠራርና አካሄድን የሚመለከቱ የህግ፣የመመስረቻ ጽሑፍ ወይም የመተዳደሪያ ደንብ ጥሰቶች ጋር የሚያያዙ እንጂ ሌሎች ከላይ የተጠቀሱ ከባለአክሲዮኖቹ መሠረታዊ የሆነ የአባልነት መብትን የሚመለከቱ ጉዳዮችን አለመሆኑን ከተለያዩ የሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች ይዘት መረዳት የሚቻል ነው፡፡በመሆኑም የማህበሩን ጉባኤ አጠራርና አካሄድን የሚመለከቱ፣የህግ፣የመመስረቻ ጽሑፍ ወይም ከመተዳደሪያ ደንብ ጥሰቶች ጋር በተገናኘ በአንቀጽ 416(2) ስር የሶስት ወር ይርጋ ድንጋጌ ተፈፃሚ መሆኑን የሚያመለክቱ ስለመሆናቸው የሚያስገነዝብ ነው፡፡

በሌላም በኩል በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ የአባልነትን መብት መጣስ ማስከተሉን መነሻ በማድረግ የሚቀርብ አቤቱታ በተመለከተ በንግድ ህጉ የተደነገገ የክስ ማቅረቢያ ጊዜ ያልተደነገገ በመሆኑ በፍትሐብሔር ህጉ ስለልዩ ውሎች የተደነገገው ልዩ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ከውልም ሆነ ከውል ውጭ የሚመነጭ ማናቸውም ስምምነት በፍትሐብሔር ህጉ ስለውሎች በጠቅላው በተደነገገው መርህ መሰረት የሚመራ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1677 ድንጋጌ ይዘት ያሳያል፡፡ ስለውሎች በጠቅላላው

ከሚደነግገው የህጉ ክፍል ውስጥ ከተመለከቱት መሰረታዊ መርሆዎች ውስጥ አንዱ በቁጥር 1845 ስር ይርጋን የሚመለከት ድንጋጌ ሲሆን ድንጋጌው ስር የተመለከተው የይርጋ ጉዳዩን በቀጥታ የሚመለከት የይርጋ ደንብ በግልፅ ባልተመለከተባቸው ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት ያለው ስለመሆኑ ከቁጥር 1677 እና 1845 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መገንዘብ ይቻላል፡፡በዚሁ መሰረት ከጉባኤ አጠራር እና አካሄድ ውጭ ባሉት ጉዳዮች ላይ የተፈፀመን የህግ አልያም የመመስረቻ ፅሁፍ ጥሰትን አስመልክቶ የማህበሩን ቃለ ጉባኤ ለማስሰረዝ የሚቀርብን ክስ የማቅረቢያ ጊዜ በህግ በግልፅ ተለይቶ ያልተመለከተ በመሆኑ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1845 ስር የተመለከተው የ10 ዓመት ይርጋ ተፈፃሚ ስለመሆኑ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 52269፣230139 እና ተመሳሳይ ውሳኔዎች ላይ አስገዳጅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት አቤቱታ ሲታይ አላግባብ ከማህበሩ እንዲንሰናበት የተወሰነ በመሆኑ ወደ ማህበሩ እንዲንመለስ፣ካልሆነ ማህበሩ ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ ኦዲት ተደርጎ ድርሻ እና ትርፋችን ታስቦ እንዲከፈለን የሚል ሲሆን አመልካቾች ያቀረቡት አቤቱታ ከጉባኤው አጠራርና የመመስረቻ ጽሑፍ ወይም የመተዳደሪያ ደንብን የሚመለከቱ ሳይሆኑ በመሰረታዊነት በአክሲዮን ማህበር መስራችነታቸው ከማህበሩ ያላቸውን የመብት ለማስከበር ሲባል አቤቱታ ማቅረባቸውን የሚያመለክት ነው፡፡ በዚህ መንገድ ማህበሩ ውስጥ መብት ለማስከበር ሲባል የሚቀርብ ክስ በቀድሞ ንግድ ህግ አንቀጽ 416(2) መሠረት የማይሸፈንና በሶስት ወር ይርጋ ቀሪ ሊሆን የማይችል ስለመሆኑ የተመለከተ ሲሆን በአመልካቾች ተቃዉሞ የቀረበበት ቃለ ጉባኤ የተላለፈው ሰኔ 22 ቀን 2006 ዓ.ም ሲሆን ክስ ያቀረቡት ሚያዝያ 12 ቀን 2009 ዓ.ም በመሆኑ ከላይ እንደተመለከተው የ10 ዓመት ይርጋ ያላለፈ ሆኖ እያለ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የቀረበው አቤቱታ በቀድሞ የንግድ ህግ አንቀጽ 416(2) መሠረት በሶስት ወር ይርጋ የሚታገድ ነው በሚል ተሰጠው ውሳኔ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4)(ለ)(ሸ) እና 10(1)(ለ) መሠረት መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 211531 የካቲት 27 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የአመልካቾችን ክስ በይርጋ ውድቅ በማድረግ በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የዴና አካባቢው ቋሚ ችሎት በመ/ቁ 0105399 ሰኔ 17 ቀን 2013 ዓ.ም የተሰጠውን ውሳኔ በመሻር የሰጠው ውሳኔ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ -ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1)(ለ) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የአመልካቾች ክስ ከመሰረታዊ የባለአክሲዮንነት መብት ጋር የተያያዘ በመሆኑ በቀድሞ የንግድ ህግ አንቀፅ 416(2) ድንጋጌ ስር በተመለከተው በሶስት ወር የይርጋ ጊዜ የሚታገድ አይደለም ብለናል፡፡

3. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ የግራ ቀኙን ክርክር መሠረት በማድረግ በፍሬ ነገሩ ላይ የመሰለውን እንዲወስን በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(2) መሠረት መልሰንለታል፡፡

4. የዚህን ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

**ማስታወሻ፡** - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 249104

የካቲት 24 ቀን 2017ዓ/ም

**ዳኞች፡-** ብርሃኑ አመነው

ሽመክት አሰፋ

በእውቀት በላይ

ሀፊዝ አባጆማል

ማርታ ተካ

አመልካች፡- የየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 7 ቀበሌ 11/12/08 ሸማቾች ኃ/የተ/ሕ/ሥ/ማ

ተጠሪዎች፡-
1. አቶ እንኮሳ አመንቴ ሱፋ
2. አቶ ጌታቸው አየለ
3. አቶ ሰይፋ አለማየሁ ቶሌራ
4. ወ/ሮ ጽጌ ሰመረ ገ/መድህን
5. ወ/ሮ ፀሐይነሽ ተካልኝ ወልዴ
6. ወ/ሮ ገረሙ ወልዴ ካብቲመር
7. ወ/ሮ ፀሐይ ታደስ ጌታነህ
8. ወ/ሮ ፅጌ በቀለ አጋ
9. ወ/ሮ በለጡ አደራ ዘወልዴ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

**ማስታወሻ፡** - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሰኔ 14 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፌው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 156258፤የካቲት 29 ቀን 2013ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 268833፤ግንቦት 15 ቀን 2015 ዓ.ም መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የንብረት መፋለምን ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን ተጠሪዎች ከሳሾች፤ የአሁኑ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁን ተጠሪዎችች በሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- በየካ አውራጃ ከፍተኛ 16 ቀበሌ 08 የቀድሞው የቀበሌ አመራሮች የተጠሪዎችን የመኖሪያ ቤት ችግር ለመቅረፍ በማሰብ ከህብረት ሥራ ማህበር ብር 29.000 (ሃያ ዘጠኝ ሺህ ብር) በብድር መልክ ወጪ ተደርጎ ቤት እንድንገነባ ተፈቅዶልን ቤቶቹን በመገንባት የብድር ገንዘብም ተመልሷል፤ ተጠሪዎችን ጨምሮ ሌሎች ነዋሪዎች በራሳችን ገንዘብ ቤቶቹን አፍርሰን እንደሰራን በወቅቱ የነበሩ የአመልካች አመራሮች አረጋግጠው በሰነድ ማስረጃ ሰጥተውናል፤ ተጠሪዎች ከ1982/1983 ጀምሮ በሰነድ አልባ በመኖሪያ ቤቶቹን ገንብተን እየኖርን እያለን ከ20 ዓመታት በኋላ አመልካች ለተጠሪዎች ያሰበ በማስመሰል ከፊሎቹን የተጠሪዎች ቤቶች ለልማት ሊፈርሱ ስለሚችሉ የጋራ መኖሪያ ቤት መንግስት እንዲሰጣችሁ እና ቀበሌው እንዲያውቃችሁ በማለት ከሱ ጋር የቤት ኪራይ ውል እንድንዋዋል ሲጠይቀን ተጠሪዎችም የአመልካች ህብረት ሥራ ማህበር አባላት በመሆናችን እና መንግስታዊ ተቋም ነው ብለን በማመን ከ2ኛ ተጠሪ በስተቀር ከአመልካች ጋር የቤት ኪራይ ውል ልንፈርም ችለናል፤ተጠሪዎች የይዞታ ማረጋገጫ ለመቀበል በሂደት ላይ እያለን አመልካች ከህግም ሆነ ከውል የመነጨ መብት ሳይኖረው እንዳይፈጸም አድርጓል፤ አመልካች ተጠሪዎችን በማታለል ባስፈረመን የኪራይ ውል መነሻነት ከዚህ ቀደም በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ኪራዩን ከፍለው ቤቱን ያስረክቡኝ በማለት ክስ አቅርቦ ተጠሪዎች ቤቱን እንድናስረክብ ተወስኗል፤ ሆኖም ከመነሻው ቦታው በጎርፍ ምክንያት ለህይወታችን እስጊ በመሆኑ ልዋጭ ቦታ እንዲሰጠን የሚመለከተውን አካል ጠይቀን ሲሰጠን በቦታው ላይ ቀበሌው ቤት መስራት ካልቻለ ነዋሪዎች በራሳችን ወጪ እንድንሰራ በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት በራሳችን ወጪ ቤት ገንብተን በስማችን ውሃ፣ መብራት እና መሰል መሰረታዊ አገልግሎቶችን አስገብተን የምንኖርበት ቤት በመሆኑ ቤቶቹ የተጠሪዎች ናቸው ተብሎ ይወሰንልን በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁን አመልካች በሰጠው መልስ አከራካሪውን ቤቶች በተመለከተ ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክስ አቅርበን ተጠሪዎች ቤቱን ለቀው እንዲወጡ የተወሰነባቸው በመሆኑ ድጋሚ ክስ ሊያቀርብ አይገባም፤ተጠሪዎች አከራካሪ በሆኑት ቤቶች ላይ መብት እና ጥቅም እንዳላቸው ሳያረጋግጡ ያቀረቡት ክስ ነው፤ ተጠሪዎች የኪራይ ውሉ እንዲፈርስ ያቀረቡት ክስ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1810(1) መሰረት በይርጋ ይታገዳል የሚሉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማስቀደም በፍሬ ነገሩ ላይ ደግሞ አከራካሪው

ቤቶች ቀደም ሲል በቀበሌ የሕዝብ ሱቅ ባላደራ ኮሚቴ ስር ሲተዳደሩ የቆዩ መሆናቸው አመልካች ማህበር ከተቋቋመ በኂላ በደንብ ቁጥር 46/2004 መሰረት ቤቶቹን ተረክቦ በማስተዳደር ላይ እንደሚገኝ፤ አመልካች በቤቱ ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ያላወጣው በጂ.አይ.ኤስ ካርታ ላይ የቀበሌ ቤት ተብለው በመመዝገባቸው ምክንያት መሆኑን፤ተጠሪዎችች ቤቶቹን ገንዘብ ተበድረው ስለመስራታው ያቀረቡት ማስረጃ የለም፤ ተጠሪዎች ከአመልካች ጋር ከ1982 ዓ.ም ጀምሮ በእነዚህ ቤቶች የቤት ኪራይ ውል ተዋውለው በደረሰኝ ኪራይ ሲከፍሉ ቆይተው የቤቶቹ ባለቤቶች እንደሆኑ አድርገው ያቀረቡት ክስ ወድቅ ሊደረግ ይገባል በሚል ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም በአመልካች የተነሱት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች በብይን ውድቅ በማድረግ በፍሬ ነገሩ ላይ ደግሞ የግራቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኃላ ለክርክር መነሻ የሆኑት ቤቶች ማህደር እና ከሚመለከተው የአስተዳደር አካልም ስለጉዳዩ ተጣርቶ እንዲቀርብለት ካደረገ በኃላ እንደአጠቃላይ የቀረበው ክርክርና ማስረጃ መርምሮ በመ/ቁ 156258፤ የካቲት 29 ቀን 2013ዓ.ም ሲወስን፡- ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቦታ ከስር መሰረቱ ለተጠሪዎች መኖሪያነት በወቅቱ በነበረው የመንግስት አስተዳደር የተመቻቸ እና የተሰጠ መሆኑ፤አከራካሪዎቹ ቤቶች ተጠሪዎች በራሳቸው ገንዘብ ገንብተው ከ 24 ዓመት በላይ እየኖሩበት መቆየታቸው በ2007 ዓ.ም ለተጠሪዎች የቦታ ልኬት መደረጉ፤ የኪራይ ውሉ በሚመለከትም አመልካች ለተጠሪዎች የገነባችሁት ቤቶች ሰነድ አልባ ስለሆኑ በልማት ቢፈርስባችሁ ምትክ ቦታ ኮንዶሚኒየም አታገኙም ስላላቸው የኪራይ ውሉን ሊፈርሙ እንደቻሉ በማስረጃ ሊረጋገጥ መቻሉ እንዲሁም አመልካች ለተጠሪዎች ቤት ገንብቷል ቢባል እንኳን ተጠሪዎች አመልካች ሳይቃወም ቦታውን አስፋፍተው ቤቶች በመገንባት ለረጅም ጊዜ በገነቡዋቸው ቤቶች  መብራት እና ውሃ ቆጣሪ አስገብተው የሚኖሩ በመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 1179(1) መሰረት የቤቶቹ ባለቤት እንደሚሆኑ፤ አመልካች ቤቶች የራሴ ናቸው በሚል ቢከራከርም ቤቶቹን በምን አግባብ እንዳገኘ አላስረዳም፤ በጊዜው በነበረው አሰራር ለህግ ሰውነት ላለው እንደ አመልካች ማህበር ለንግድ ስራ ካልሆነ በስተቀር ለመኖሪያ ቦታ የሚስጥበት ሕግም ሆነ አሰራር አለመኖሩን፤አመልካች ለተጠሪዎች ቤት ለግንባታ ወጪ አውጥቻለሁ ካለ ያወጣውን ወጪ እንዲተኩለት ከመጠየቅ በቀር አመልካች የቤቶች ባለቤት የሚሆንበት የህግ አግባብ አለመኖሩን ጠቅሶ ለክርክሩ ምክንያት የሆኑት ቤቶች የተጠሪዎች የግል ቤቶች በመሆናቸው አመልካች መብት የለውም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ለክርክሩ ምክንያት በሆኑት ቤቶች ላይ በግራ ቀኙ መካከል የኪራይ ውል መኖሩ አልተካደም፤ አመልካች ይህንን የኪራይ ውል መሰረት በማድረግ ኪራይ እንዲከፈለው እና ቤቶቹን ለቀው እንዲወጡ በተጠሪዎች ላይ ክስ አቅርቦ አስወስኗል፤ ተጠሪዎች የኪራይ ውሉን የፈረሙት በአመልካች ተታልለው ስለመሆኑ ባላስረዱበት፤የኪራይ ውሉ ባላስፈረሱበት እንዲሁም በተለያዩ መዝገቦች የቤቱ ባለቤት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

አመልካች መሆኑ ተረጋግጦ ተጠሪዎች ቤቶቹ ለቀው እንዲያስረክቡ ተወስኖ ባለበት ሁኔታ ቤቶቹ የተጠሪዎች ናቸው ተብሎ መወሰኑ አግባብ የለም በማለት የስር መጀመርያ ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ በመሻር በመ/ቁ 268833፤መስከረም 28 ቀን 2014ዓ.ም ወስኖ የነበረ ቢሆንም ተጠሪዎች ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም እስከ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ተከራክረው በዚሁ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ግራቀኙን ካከራከረ በኃላ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ በመሻር አመልካች ኪራይን መሠረት በማድረግ በተጠሪዎች ላይ አስቀድሞ ባቀረበው ክስ መነሻነት ተጠሪዎች የቤቱን ኪራይ ከፍለው ቤቱን እንዲያስረክቡ መወሰኑ ተጠሪዎች በቤቶቹ ላይ የሚያቀርቡትን የመፋለም ክርክር የሚያስቀር አለመሆኑን ጠቅሶ ጉዳዩን በዚህ አግባብ በማየት አመልካችም ሆነ ተጠሪዎች በንብረቱ ባለቤትነት ላይ ያቀረቡትን ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ በስር የመጀመሪያው ደረጃ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ መሆን አለመሆን ላይ በይግባኝ ሰሚነት ስልጣኑ ውሳኔ ይስጥበት በማለት በሰ/መ/ቁ 222830፤ ሕዳር 27 ቀን 2013ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ በመመሪያ መልሶለታል፡፡

የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሰበር ችሎቱ በመመሪያ ከመለሰለት በኃላ አመልካችም ሆነ ተጠሪዎች በንብረቱ ባለቤትነት ላይ ካቀረቡትን ክርክር እና ማስረጃ አንጻር በስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ መሆን አለመሆኑን በይግባኝ ሰሚነት ስልጣኑ መርምሮ የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ የሚነቀፍ አለመሆኑን ጠቅሶ ውሳኔውን በማጽናት በመ/ቁ 268833፤ ግንቦት 15 ቀን 2015ዓ.ም ወስኗል፡፡

አመልካች ለዚህ ሰበር ችሎት ሰኔ 14 ቀን 2015ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት ሰበር ቅሬታም ተጠሪዎች ከዚህ በፊት ውዝፍ ያለባቸው ኪራይ ከፍለው እነዚሁ ቤቶች እንዲለቁ በአዲስአበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተወሰነ በመሆኑ በፍርድ ያለቀ ነው በሚል ያቀረብነው መቃወሚያ በስር ፍርድ ቤቶች ውድቅ መደረጉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ.ቁ 5 እና ሰ/መ/ቁ 62330 የተሰጠው የህግ ትርጉም የሚጥስ መሆኑን፤ ተጠሪዎች ከአመልካች ጋር በ1982/1983 ጀምሮ ያደረጉት ኪራይ ውል ተገደን ነው ወይም በማታለል ነው የሚሉ ከሆነም ውሉ እንዲፈርስ በ10 አመት ውስጥ መጠየቅ ሲገባቸው ከ30 አመታት በኃላ የቀረቡት ክስ በይርጋ ቀሪ ሊሆን ይገባል በሚል ያቀረብነው መቃወሚያ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ሳያየው አልፎ መወሰኑ ስህተት መሆኑ፤አከራካሪዎች ቤቶች ባለቤትነት በተመለከተ ከዚህ በፊት ክርክር ተደርጎ የአመልካች መሆናቸው ተረጋግጦ በአዲስአበባ ከተማ አስተዳደር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተወሰነውን እስከ ሰበር ሰሚው ፍ/ቤት ፀንቶ ባለበት ሁኔታ ይህንኑ ውሳኔ ውጤት አልባ በሚያደርግ መልኩ ሊወሰን እንደማይችል በሰ/መ/ቁ 91622 የሰጠው ገዢ የህግ ትርጉም ጠቅሰን ያቀረብነው መከራከርያ ሳይታይ መወሰኑ ተገቢ አለመሆኑ፤ አመልካች እነዚህ ቤቶች ያገኘው በደንብ ቁጥር 46/2004 መሰረት መሆኑና አከራካሪዎች ቤቶች በቀድሞው ከፍተኛ 16 ቀበሌ 08 የህዝብ ሱቅ ባለአደራ ቦርድ ሲያስተዳድራቸው የቆየ

መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጦ እያለ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይህንኑ ታልፎ የእነዚህ ቤቶች ባለቤቶች ተጠሪዎች ናቸው ሲል የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ማጽናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ፡- ተጠሪዎች አከራካሪዎቹ ቤቶች ከአመልካች ጋር በነበራቸው የኪራይ ውል መነሻነት ሲጠቀሙ የነበረ መሆኑ ከመረጋገጡ አንጻር ውሉ ባልፈረሰበት ሁኔታ ቤቶቹ የተጠሪዎች ናቸው ተብሎ መወሰኑ ተገቢ መሆን አለመሆኑ በሰ/መ/ቁ 48012፣ 90361 ከተሰጡት ገዢ ውሳኔዎች አንጻር ለመመርመር የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

ተጠሪዎች ታህሳስ 14 ቀን 2017 ዓ.ም ጽፈው የሰጡት መልስ ይዘት በአጭሩ፡- በአመልካች በኩል የተጠሪዎች ክስ አስቀድሞ በፍርድ ባለቀ ጉዳይ በድጋሚ የቀረበ ነው፣ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሊሆን ይገባል በሚል የሚያቀርቡት ክርክር ከዚህ በፊት ሰበር ሰሚ ችሎቱ በመመሪያ ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ሲመልስ ግራቀኙ ከኪራይ ውል ጋር በተያያዘ ተከራክረው ተጠሪዎች ኪራይ ከፍለው ቤቶቹ እንዲያስረክቡ መወሰኑ ተጠሪዎች ቤቶቹ ላይ የሚያቀርቡትን የመፋለም ክርክር የሚያስቀር አለመሆኑን የወሰነ በመሆኑ በዚህ ረገድ የሚያቀርቡት ቅሬታ ነጥብ ተገቢ እንዳልሆነ እንዲሁም በወቅቱ የነበሩት የአመልካች አመራሮች ተፈቅዶልን አከራካሪዎች ቤቶች ሙሉ በሙሉ ተጠሪዎች ስለመሰራታችን፣ ከ1982ዓ.ም ጀምሮ እየኖርንባቸው እንደምንገኝ በስር ፍርድ ቤቶች በማስረጃና በህግ አግባብ በማረጋገጥ ቤቶች ባለቤቶች መሆናችን በማረጋገጥ የሰጡት ውሳኔ ተገቢ በመሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የግራቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በስር ፍርድ ቤቶች ለክርክሩ ምክንያት የሆኑት ቤቶች የተጠሪዎች የግል ቤቶች በመሆናቸው አመልካች መብት የለውም በሚል መወሰኑ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን ከግራቀኙ ክርክር፣ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ከክርክሩ ለመረዳት እንደተቻለው ተጠሪዎች የነበረባቸውን የቤት ችግር ለመቅረፍ ታስቦ በወቅቱ በነበሩ የቀበሌ አመራሮች ተፈቅዶላቸው በራሳቸው ገንዘብ ቤቶቹን አፍርሰው በመገንባት ከ1982 ዓ.ም ጀምሮ እየተጠቀሙበት የሚገኘውን ቤት አመልካች ቀበሌው እንዲያውቃችሁ በሚል አታሎ የቤት ኪራይ ውል እንዲዋዋሉን በማድረግ ኪራዩን ከፍለው ቤቱን ያስረክቡኝ በማለት ክስ አቅርቦ ያስወሰነባቸው ቢሆንም ከመነሻው ይዞታው በጎርፍ ምክንያት ለህይወታችን እስጊ በመሆኑ ልዋጭ ቦታ እንዲሰጣቸው

የሚመለከተውን አካል ጠይቀው ሲሰጣቸው ቀበሌው ቤት መስራት ባለመቻሉ ተጠሪዎች በራሳቸው ወጪ እንዲሰሩ ተፈቅዶላቸው በራሳቸው ወጪ ቤት ገንብተው በስማችን ውሃ፣ መብራት እና መሰል መሰረታዊ አገልግሎቶችን አስገብተው የሚኖርበት ቤት መሆኑን ጠቅሰው ቤቶቹ የተጠሪዎች ናቸው ተብሎ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት ሲጠይቁ በአመልካች በኩል ከዚህ በፊት ውዝፍ ያለባቸው ኪራይ ከፍለው እነዚሁ ቤቶች እንዲለቁ በአዲስአበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተወሰነ በመሆኑ በፍርድ ያለቀ ነው፤ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሊሆን ይገባል የሚሉ መቃወሚያዎች በማስቀደም በፍሬጉዳይ ላይ በሰጠው መልስም አከራካሪዎች ቤቶች በቀድሞው ከፍተኛ 16 ቀበሌ 08 የህዝብ ሱቅ ባለአደራ ቦርድ ሲያስተዳድራቸው የቆየና አመልካች እነዚህ ቤቶች በደንብ ቁጥር 46/2004 መሰረት የሚያስተዳድረው እንጂ የተጠሪዎች የግል ቤቶች አደሉም በሚል መከራከሩን ያሳያል፡፡

የስር ፍርድ ቤቶችም ለክሱ ምክንያት የሆኑት ቤቶች ከስር መሰረቱ ይዞታው ለተጠሪዎች መኖሪያነት በወቅቱ በነበረው የመንግስት አስተዳደር የተመቻቸ እና የተሰጠ እንደሆነ፤ ተጠሪዎች በዚሁ ይዞታ ላይ በራሳቸው ገንዘብ ቤቶች ገንብተው ከ 24 ዓመት በላይ እየኖሩበት መቆየታቸው በ2007 ዓ.ም ለተጠሪዎች የቦታ ልኬት መደረጉ፤ የኪራይ ውሉ በሚመለከትም አመልካች ለተጠሪዎች የገነባችሁት ቤቶች ሰነድ አልባ ስለሆኑ በልማት ቢፈርስባችሁ ምትክ ቦታ ኮንዶሚኒየም አታገኙም ስላላቸው የኪራይ ውሉን ሊፈርሙ እንደቻሉ በማስረጃ ለማረጋገጥ መቻሉን እንዲሁም ተጠሪዎች አመልካች ሳይቃወም ቦታውን አስፋፍተው ቤቶች በመገንባት ለረጅም ጊዜ በገነቡዋቸው ቤቶች መብራት እና ውሃ ቆጣሪ አስገብተው የሚኖሩ በመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 1179(1) መሰረት የቤቶቹ ባለቤት እንደሚሆኑ በአንጻሩ አመልካች ቤቶች የራሴ ናቸው በሚል ቢከራከርም ቤቶቹን በምን አግባብ እንዳገኘ አለማስረዳቱ በጊዜው በነበረው አሰራር እንደ አመልካች የህግ ሰውነት ላለው ሽማቾች ማህበር ለንግድ ስራ ካልሆነ በስተቀር ለመኖረያ ቦታ የሚስጥበት ሕግም ሆነ አሰራር የለም የሚል ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ በአመልካች በኩል በሰበር ቅሬታው ላይ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በሚል አጥብቆ የሚከራከርበት ዋነኛው ነጥብ ተጠሪዎች ከዚህ በፊት ውዝፍ ያለባቸው ኪራይ ከፍለው እነዚሁ ቤቶች እንዲለቁ በአዲስአበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተወሰነ በመሆኑ በፍርድ ያለቀ ነው እንዲሁም ተጠሪዎች ከአመልካች ጋር በ1982/1983 ጀምሮ ያደረጉት ኪራይ ውል ተገደን ነው ወይም በማታለል ነው የሚሉ ከሆነም ውሉ እንዲፈርስ በ10 አመት ውስጥ መጠየቅ ሲገባቸው ከ30 አመታት በኃላ የቀረቡት ክስ በይርጋ ቀሪ ሊሆን ይገባል እንዲሁም አከራካሪዎች ቤቶች ባለቤትነት በተመለከተ ከዚህ በፊት ክርክር ተደርጎ ተጠሪዎች ቤቶቹን እንዲቀሉ በአዲስአበባ ከተማ አስተዳደር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተወሰነውን እስከ ሰበር ሰሚው ፍ/ቤት ፀንቶ ባለበት ሁኔታ ይህንኑ ውሳኔ ውጤት አልባ በሚያደርግ መልኩ አከራካሪዎች ቤቶች የተጠሪዎች የግል ቤቶች ናቸው ተብሎ መወሰኑ ተገቢነት የለውም የሚል ነው፡፡ ይህ ሰበር ችሎትም አመልካች በዚህ ረገድ የሚያቀርበው

ማስ ታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ሰበር ቅሬታ ነጥብ አግባብነት ስንመለከት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ከዚህ በፊት የስር ፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመሻር በሰ/መ/ቁ 222830፤ ሕዳር 27 ቀን 2013ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ በመመሪያ ሲመልስ ተጠሪዎች በቤቱ ላይ አለን የሚሉት መከራከሪያ በተከራይነት መብት ላይ ብቻ የተገደበ ሳይሆን ከዚህ ባለፈ ቤቶቹ በግል ገንዘባችን የተሰሩ በመሆኑ የቤቶቹ ባለቤት ነን የሚል ነው። ስለሆነም አመልካች ኪራይን መሠረት በማድረግ በተጠሪዎች ላይ አስቀድሞ ባቀረበው ክስ መነሻነት ተጠሪዎች የቤቱን ኪራይ ከፍለው ቤቱን እንዲያስረክቡ የተሰጠው ውሳኔ ተጠሪዎች በቤቶቹ ላይ የሚያቀርቡትን የመፋለም ክርክር የሚያስቀር አለመሆኑን በውሳኔው ላይ በማስፈር አመልካችም ሆነ ተጠሪዎች በንብረቱ ባለቤትነት ላይ ያቀረቡትን ሌሎች ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ በስር የመጀመሪያው ደረጃ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ መሆን አለመሆን ላይ በይግባኝ ሰሚነት ስልጣኑ ውሳኔ ይስጥበት በሚል መመለሱን ተመልክተናል። ይህ ከሆነ አመልካች አሁን በሰበር ቅሬታቸው ላይ መቃወሚያነት ያነሱዋቸው ቅሬታ ነጥቦች ሰበር ችሎቱ አስቀድሞ በመመሪያ ወደ ታች በመመሪያ ውሳኔ ያሳረፈበት ነው። እንዲሁም አመልካች የሚያነሳው የይርጋ መቃወሚያም  የተጠሪዎቸ ክስ የኪራይ ውል ለማስፈረስ የቀረበ ሳይሆን የንብረት መፋለም የሚመለከት በፍ/ብ/ሕ.ቁ 1206 መሰረት የቀረበ ክስ በመሆኑ በይርጋ ቀሪ ሊደረግ የሚችል ባለመሆኑ በዚህ ረገድ አመልካች የሚያቀርባቸው የሰበር ቅሬታ ነጥቦች ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም።

ሌላው አመልካች የቤቶች ባለቤት ሆኜ እያለ የተጠሪዎች የግል ቤቶች ናቸው ተብሎ መወሰኑ ተገቢ አደለም በሚል የሚቀርበው ቅሬታ ነጥብ አግባብነት ስንመለከት፡-

እንደሚታወቀው የንብረት ባለቤትነት የሚገኘው በጉልበትና በገንዘብ ስለመፈራቱ ሲረጋገጥ መሆኑን፣በዚህ አግባብ ሲረጋገጥ ደግሞ ሕጋዊ ጥበቃ ሊሰጠው የሚገባው መሆኑን በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 40(1) እና (2) ድንጋጌዎች ያሳያል። አንድ ሰው የአንድ ንብረት ባለቤት ነው ተብሎ በሕጉ ጥበቃ የሚደረግለት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195፣1204(1)፣1206 እንዲሁም ከላይ በተጠቀሱት ህገ መንግስታዊ ድንጋጌዎች አግባብ በግል ገንዘቡ፣እውቀቱና ጉልበቱ ያፈራው መሆኑ ሲረጋገጥ ነው። በዚህ ጉዳይ ለክሱ ምክንያት የሆኑት ቤቶች ከመነሻው በወቅቱ በነበረው የቀበሌ አስተዳደር ይዞታው ለተጠሪዎች መኖሪያነት ተሰጥቶኣቸው፤ ተጠሪዎች በዚሁ ይዞታ ላይ በራሳቸው ገንዘብ ቤቶች ገንብተው መብራት እና ውሃ በስማቸው በማስገባት ከ 24 ዓመት በላይ እየኖሩበት መቆየታቸው፤ በ2007 ዓ.ም  የቦታ ልኬት ሲደረግም ለተጠሪዎች መደረጉ፤ የኪራይ ውሉ በሚመለከትም አመልካች ለተጠሪዎች የገነባችሁት ቤቶች ሰነድ አልባ ስለሆኑ በልማት ቢፈርስባችሁ ምትክ ቦታ ኮንዶሚኒየም አታገኙም ስላላቸው የኪራይ ውሉን ሊፈርሙ እንደቻሉ ማስረጃዎችን የመስማት፤የመመርመር እና የመመዘን በህግ ስልጣን በተሰጣቸው ስር ፍርድ ቤቶች በፍሬነገር ደረጃ ተረጋግጧል። ይህ ሰበር ችሎትም ሕገመንግስቱ አንቀጽ 80 (3) (ሀ) እና ህገ መንግስቱን መሰረት አድርጎ በወጣው የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 መሰረት የተሰጠው

የዳኝነት ስልጣን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸውን ማንኛውም የመጨረሻ ውሳኔዎችን ከማረም በዘለለ ማስረጃ የመመዘን ስልጣን የሌለው በመሆኑ በስር የተረጋገጠውን ፍሬነገር እንዳለ የሚቀበለው ነው የሚሆነው፤ ከዚህ አንጻር ተጠሪዎች በአከራካሪዎች ቤቶች በራሳቸው ወጭ ገንብተው መብራት እና ውሃ በስማቸው በማስገባት ከ 24 ዓመት በላይ እየኖሩበት መቆየታቸውና በ2007 ዓ.ም የቦታ ልኬት ሲደረግም ለተጠሪዎች መደረጉ በተረጋገጠበትና አመልካች ቤቶች በራሱ ወጭ ገንብቶ ለተጠሪዎች ስለማከራየቱም ሆነ በቤቶች ላይ በህግ ጥበቃ ሊደረግለት የሚችል መብት ያለው ስለመሆኑ በማንኛውም መንገድ ባላስረዳበት ሁኔታ ቤቶች የራሴ ናቸው በሚል የሚያቀርበው መከራከርያ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችልበት የሕግ አግባብ አይኖርም፡፡

ሲጠቃለል ለክሱ ምክንያት የሆኑት ቤቶች የተጠሪዎች የግል ቤቶች በመሆናቸው አመልካች መብት የለውም በሚል በስር ፍርድ ቤቶች መወሰኑ ተገቢ ነው ከሚባል በቀር የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት አላገኘንበትም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 156258፤ የካቲት 29 ቀን 2013ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 268833፤ግንቦት 15 ቀን 2015ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9/1 መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
3. ውሳኔው መጋቢት 11 ቀን 2017ዓ/ም ተነቧል፡፡

   መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ.መ.ቁ250332

የካቲት 25 ቀን 2017

ዳኞች፡ ብርሃኑ አመነው

ሽመክት አሰፋ

በዕውቀት በላይ

መላኩ ካሳዬ

አየለ ማሞ

አመልካች፡ ወ/ሮ አዳነች ሞኝነት ተወካይ አቶ ሞኝነት ጀምበር ቀርበዋል

ተጠሪ፡ አቶ ይልቃል አቤ ቀርበዋል

መዝገቡ የተቀጠረው የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ ተገቢውን ለመስራት ሲሆን ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ይህ የሰበር መዝገብ ተከፍቶ ለዚህ ሰበር ችሎት የቀረበው የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 0153728 በ9/02/2015ዓ.ም እና የአብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጠር 01-59960 ጥር 16 ቀን 2015ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን ገልጸው አመልካች 05/11/2015ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ በተወካያቸው አማካይነት በማቅረባቸው ነው፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ለዚህ የሰበር ክርክር ምክንያት የሆነው ክርክር የተጀመረው በአማራ ክልል ባሶ ሊበን ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን በወረዳው ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ በባሶ ሊበን ወረዳ ፍርድ ቤት ላይ ባቀረቡት ክስ አመልካች የተጠሪ አያት የሟች እማሆይ ጥሩ በላይ የቤተሰብ አባል ሳትሆንና ከሟቿ ጋር በአንድ ላይ ሆኖም ሆነ ከውጭ ሆኖ ሟቿን ሳትጦርና ሳትንከባከብ እንደጦረች እንደተንከባከበችና የሟቿ የቤተሰብ አባል እንደሆነች አስመስላ የሟቿን የእድሜ ባለፀጋነትን እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ሟቿ ከቢሮ ሳይሄዱ እንደሄዱና በስጦታ እንዳስተላለፉላት በማድረግ ከመሬት ባለሙያ ጋር በመመሳጠር በ13/10/1998ዓ.ም የስጦታ ውል በማስሞላት የኑዛዜ ስጦታውን በመሬት አስተዳደር ጽ/ቤት በማስመዝገብ የኑዛዜ ስጦታ አለኝ በማለት አጭበርብራ ማስረጃ እንደያዘች" ገልጸው የመሬት ስጦታ ውሉም ሆነ ማስረጃው እንዲሰረዝላቸው ዳኝነት በመጠየቅ ክስ አቅርበዋል፡፡

ለዚህ የተጠሪ ክስ አመልካች መልስ እንዲሰጡ በፍ/ቤቱ ታዘው የመሬት ስጦታው በመሬት አስተዳደር ጽ/ቤት ተመዝግቦ ከተሰጣቸው 16 ዓመታትን ያስቆጠረ በመሆኑ ከ16 ዓመት በኋላ የቀረበው የስጦታ ውል ይሰረዝልኝ ክስ በይርጋ እንደሚታገድ ገልጸው መጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያና በፍሬ ነገሩ ረገድም ሟቿ የአመልካችም አያት በመሆናቸው ‹‹ ስጦታውን የተቀበልሁት በተጭበረበረ መንገድ ሳይሆን ስጦታ ሰጭ በሙሉ ጤንነት ላይ ሆና የእድሜ መግፋት ሳይኖርባት ትጦረኛለች ትንከባከበኛለች በማለት በባሶ ሊበን ወረዳ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ፊት ለፊት ቀርባ ያስመዘገበችልኝ በመሆኑ›› ክሱ በሐሰት እንደቀረበባቸው ገልፀው የተጠሪን ክስ ሙሉ በሙሉ ክደው መልስ ሰጥተዋል፡፡

ከዚህ በኋላ የወረዳው ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ከሰማና ስለ ስጦታ ውሉ ከወረዳው የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት በትዕዛዝ ጠይቆ ተጨማሪ ማጣራት ካደረገ በኋላ ምንም እንኳ ስጦታው የተሰጠውና በወረዳው የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ቀርቦ የተመዘገበው በ13/10/1998 ዓ.ም ቢሆንም ሟቿ የሞቱት ግን የካቲት 10 ቀን 2012ዓ.ም በመሆኑና ተጠሪ በወራሽነት መብታቸው ለመሥራት የሚችሉት ሟቿ ከሞቱበት ጊዜ ጀምሮ መሆኑን ገልጾ በአመልካች የቀረበውን ይርጋ መቃወሚያ ውድቅ ያደረገ ሲሆን ፍሬ ነገሩን በተመለከተ ግን አመልካች ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ ከሟቿ ጋር በመሆን የክርክሩን ይዞታ በእጃቸው አድርገው ሲጠቀሙና ሟቿንም ሲጦሩ የነበረ ስለመሆኑ በተጠሪ ምስክሮች ጭምር የተመሰከረ ከመሆኑም ባሻገር አመልካች ይዞታውን የያዙበትን አግባብ በተመለከተም ምንም እንኳ በምን አግባብ ሊይዙ እንደቻሉ እንደማያውቁ የተጠሪ ምስክሮች ቢመሰክሩም ውሉ ሲደረግ በቦታው በእማኝነት የተገኙት ሰዎች እንዲሁም በወቅቱ የሥጦታ ውሉን የመዘገቡት የወረዳው የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት የሥራ ኃላፊ የአመልካች የመከላከያ ምስክሮች ሆነው ቀርበው በሰጡት የመከላከያ ምስክርነት የግራ ቀኝ አያት የሆኑት ሟች እማሆይ ጥሩ በላይ የተጠሪ 4ኛ ምስክር የሆኑት

ወላጅ አባታቸው ጭምር ባሉበት ቦታ በ13/10/1998ዓ.ም በመኖሪያ ቤታቸው ሆነው የክርክሩን ይዞታ ለአመልካች በስጦታ እንደሰጡ ፣ በስጦታ ውሉ ላይም ስጦታ ሰጭ፣ ስጦታ ተቀባይና የተጠሪን ወላጅ አባት ጨምሮ ሁሉም ምስክሮች እንደፈረሙ፣ ከዚያ በኋላ ግራ ቀኙና በወረዳው ፍ/ቤት የተጠሪ 4ኛ ምስክር ሆነው የቀረቡት የተጠሪ ወላጅ አባት በአንድ ላይ ወደ ወረዳው የመሬት አስተዳደር ጽ/ቤት ሄደው እቤት የተዘጋጀው ውል ቀርቶ የወረዳው የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ራሱ ባዘጋጀው ፎርም ላይ የውሉን ይዘት ሞልቶ ግራ ቀኙን በማስፈረም ውሉን እንደመዘገበና ፣ አመልካች እስከ ሟቿ እለተ ሞት ድረስ ሟቿን ሲጦሩና ሲንከባከቡ እንዲሁም የክርክሩን ይዞታም በእጃቸው አድርገው ሲጠቀሙ እንደነበረ ገልጸው እንደመሰከሩና በወረዳው የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት የተመዘገበው የስጦታ ውልም ከጽ/ቤቱ በትዕዛዝ ቀርቦ በአመልካች የመከላከያ መልስ ላይ የተገለጸው ክርክር እውነት መሆኑ እንደተረጋገጠ ገልጾ የተጠሪን ክስ ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

ተጠሪ በዚህ የባሶ ሊበን ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ እንዲሁም አመልካች ደግሞ በወረዳው ፍ/ቤት ያቀረቡት የይርጋ ክርክር ውድቅ ተደርጎ በተወሰነው ላይ የመስቀልኛ ይግባኝ ለምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ይግባኝና መስቀለኛ ይግባኝ በመዝገብ ቁጥር 0153728 መርምሮ በአመልካች የቀረበውን መስቀለኛ ይግባኝ ውድቅ በማድረግና በአንጻሩ ምንም እንኳ አመልካች ሟቿን ሲጦሩ እንደነበረ፣ ሟቿ ስጦታውን ወደውና ፈቅደው እንደሰጡ ፣ የሥጦታ ውሉም በወቅቱ ወደ ወረዳው የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ቀርቦ ተመዝግቦ እንደጸደቀና አመልካች ስጦታው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ የክርክሩን ይዞታ በእጃቸው አድርገው ሟችን ሲጦሯቸውና ራሳቸውም ሲጠቀሙ እንደነበረ ቢረጋገጥም በስጦታ የተሰጠው የማይንቀሳቀስ ንብረት ሆኖ በስጦታ ውሉ ላይ ግን ስጦታ ሰጭ፣ ስጦታ ተቀባይና ስጦታውን የመዘገበው የወረዳው የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት የሥራ ኃላፊ ብቻ የፈረሙ በመሆኑ ውሉ የማይንቀሳቀስ ንብረትን የሚመለከተው የስጦታ ውል ሊደረግ የሚገባውን ፎርም ያልጠበቀ መሆኑን ገልጾ የወረዳውን ፍ/ቤት ውሳኔ በአብላጫ ድምጽ በመሻር ወስኗል፡፡ በመቀጠልም በዚህ ውሳኔ ላይ የአሁን አመልካች ያቀረቡትን ይግባኝ የመረመረው የአብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ክርክሩ የገጠር መሬት ይዞታን የሚመለከት ሆኖ ስጦታው በተደረገበት ወቅት በሥራ ላይ የነበረው የክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 133/1998 የገጠር መሬት ስጦታ ውል በጽሑፍ ተደርጎ ለወረዳው የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ቀርቦ መመዝገብ እንደሚኖርበት ብቻ ከሚደነግግ በቀር ሌላ ተጨማሪ ፎርምን የማይጠይቅ ሆኖ እያለና ለክርክሩ ምክንያት የሆነው የስጦታ ውል ሕጋዊነትም ከዚህ ልዩ ሕግ አኳያ ብቻ ሊታይ እየተገባ ከፍተኛው ፍ/ቤት ግን የፍትሐብሔር ሕጉን ድንጋጌዎችን በመጥቀስ ውሉ ፎርምን የጠበቃ እንዳይደለ ገልጾ መወሰኑ አግባብ እንዳይደለ ገልጾ የከፍተኛውን ፍ/ቤት ውሳኔ ሽሮታል፡፡ በአንጻሩ በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ በተጠሪ የቀረበውን የሠበር አቤቱታ የመረመረው የአብክመ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ

ችሎት የሠበር አቤቱታውን ተቀብሎ በአቤቱታው ላይ ግራ ቀኙን ካከራከራቸው በኋላ በጉዳዩ ላይ ተፈጻሚነት ያለው የፍትሐብሔር ሕጉ ሳይሆን የአብክመ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ እንደሆነ ተገልጾ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተያዘው አቋም ትክክል ቢሆንም በተያዘው ጉዳይ ምንም እንኳ የስጦታ ውሉ በ13/10/1998 ተደርጎ በዕለቱ ለወረዳው የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ቀርቦ የተመዘገበ ቢሆንም ሟቿ የሞቱት ግን በ2012ዓ/ም በመሆኑ የሥጦታ ውሉ ሕጋዊነት ሊመረመር የሚገባው ውሉ በተደረገበትና በተመዘገበበት ወቅት በሥራ ላይ ባለው የክልሉ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 133/98 አኳያ ሳይሆን ሟቿ በሞቱበት ወቅት በሥራ ላይ ባለው አዋጅ ቁጥር 252/2009 አኳያ እንደሆነና ይኼው አዋጅ ደግሞ የገጠር መሬት ስጦታን የሚመለከት ውል ግልጽ ኑዛዜ የሚደረግበትን የውል አጻጻፍ ሥርዓት (ፎርም) ተከትሎ መደረግ እንዳለበት እንደሚደነግግ ገልጾ የክልሉን ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የባሶ ሊበን ወረዳ ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻር የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

በመሆኑም አመልካች ይህ የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የአብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስለመሆኑ በአቤቱታቸው ላይ ያነሱት ዋና የቅሬታ ነጥብ ተጠሪ የስጦታ ውሉን በመቃወም ክስ ያቀረቡት ውሉ ከተደረገና ወደ ወረዳው የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ቀርቦ ከተመዘገበ ከ16 ዓመታት በኋላ ሆኖ እያለና የይርጋ ክርክር ያቀረቡትም ወሉ ከተደረገ ከአስራ ስድስት ዓመት በኋላ ውሉን በመቃወም የቀረበው ክስ በይርጋ መታገዱን በመግለጽ እንጂ ከተጠሪ የወራሽነት መብት ጋር በተያያዘ ባልሆነበት የተጠሪ አያት የሞቱበት ጊዜ መነሻ ተደርጎ ክሱ በይርጋ አይታገድም መባሉ እንዲሁም የስጦታ ውሉ የተደረገውና የተመዘገበው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 133/1998 በሥራ ላይ በነበረበት ጊዜ ሆኖ እያለና ይኼው አዋጅ ደግሞ የገጠር መሬት ስጦታ ውል በጽሑፍ ተደርጎ በወረዳው የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት መመዝገብ እንዳለበት ከሚደነግግ በቀር በአራት ምስክሮች ፊት መደረግ እንዳለበት የማይደነግግ ሆኖ ሳለ ውሉ ከተደረገ ከብዙ ዓመታት በኋላ የወጣው የክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 252/2009 ተጠቅሶ የስጦታ ውሉ በዚህ አዋጅ ላይ የተመለከተውን ፎርም ተከትሎ እንዳልተደረገ ተገልጾ መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን የሚገልጽ ነው፡፡

ይህ የአመልካች የሰበር አቤቱታ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ተመርምሮ የስጦታ ውሉ የቀድሞው የክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 133/1998 በሥራ ላይ በነበረበት ጊዜ ሆኖ እያለ በጉዳዩ ላይ ተፈጻሚነት ያለው አዲሱ አዋጅ ቁጥር 252/2009 እንደሆነ ተገልፆ የተወሰነበት አግባብ የሕጎችን ተፈጻሚነት መርህ የተከተለ መሆን አለመሆኑ በሰበር ሰሚው ችሎት ሊታይ የሚገባ መሆኑ ተገልፆ ተጠሪ ለአቤቱታው መልስ እንዲሰጡ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡

በዚህም መሠረት ተጠሪ ቀርበው በ21/04/2017 ዓ.ም ጽፈው በሰጡት መልስ ስጦታው በሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 922/2008 መሠረት በሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ አገልግሎት ተመዝግቦ ሳይፀድቅ ለወረደው የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ቀርቦ መመዝገቡ ብቻ ስጦታውን ሕጋዊ እንደማያደርገውና ሟቿ የሞቱት የካቲት 12 ቀን 2012 ዓ.ም በመሆኑ በዚሁ የስጦታ ውል ላይ ተፈጻሚነት ሊኖረው የሚገባው ሟቿ በሞቱበት ወቅት በሥራ ላይ ያለ የአብክመ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 252/2009 እንጂ ውሉ በተፈረመበት ወቅት በሥራ ላይ የነበረው አዋጅ ቁጥር 133/1998 ባለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 252/2009 ላይ የተመለከተውን የገጠር መሬት ስጦታ ውል አደራረግ ፎርምን የማያሟላው የስጦታ ውል እንዲፈርስ ተገልጾ የተሰጠው የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትና የአብክመ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ሊባል የሚቻል እንዳይደለ ገልፀው ውሳኔው እንዲጸናላቸው በመጠየቅ መልስ ሰጥተዋል፡፡ የሰበር አመልካችም የሰበር ቅሬታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ አጥር ተደርጎ የተገለፀው ሲሆን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር አቤቱታው ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ (የማስቀረቢያ ነጥብ) እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሯታል፡፡

እንደመረመረውም የክርክሩ ይዞታ የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች አያት የነበሩት የሟች እማሆይ ጥሩ በላይ የነበረና ሟቿ በሕይወት እያሉ በ11/10/1998 በተፈረመ የስጦታ ውል ወደውና ፈቅደው ለአመልካች ሰጥተው የስጦታ ውሉም በወቅቱ ይዞታው ለሚገኙበት የባሶ ሊበን ወረዳ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀመ ጽ/ቤት ቀርቦ የተመዘገበ ስለመሆኑ ከወረዳው ፍ/ቤት ጀምሮ እስከ ክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ድረስ በየደረጃው ያሉ ፍሬ ነገረን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ሥልጣን በሕግ የተሰጣቸው ፍ/ቤቶች በተስማማ አኳኋን ያረጋገጡትና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ትክክለኛነቱን አረጋግጦ የተቀበለው ፍሬ ነገር ነው፡፡ እንደዚሁም የስጦታ ውሉ የገጠር እርሻ መሬትን የሚመለከት በመሆኑ የስጦታ ወሉ ሕጋዊነት ሊመርመር የሚገባው ከአማራ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጀ አኳያ እንጂ ከፍ/ሕግ ድንጋጌዎች እኳያ አለመሆኑ የአብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ሆነ ሰበር ሰሚ ችሎት የተስማሙበትና ይህ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም የሚቀበለው ጉዳይ ነው፡፡

በዚህ ጉዳይ ግራ ቀኙን እያከራከር ያለው ዋነኛው ነጥብ የስጦታ ውሉ ሕጋዊነት ሊመረመር የሚገባው የስጦታ ውሉ በተደረገበትና ለወረዳው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ቀርቦ በተመዘገበበት በ13/10/1998 ዓ.ም በሥራ ላይ የነበረውን የአማራ ክልል የገጠር መሬት አስተዳርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 133/1998 አሊያም ሟች እማሆይ ጥሩ በላይ በሞቱበት በየካቲት 12/2012 ዓ.ም በሥራ ላይ ያለውን የክልሉን የገጠር መሬት አስተዳዳርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 252/2009 መሠረት በማድረግ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

የመሆኑ ጉዳይ ነው፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያትም ሁለቱ አዋጆች የገጠር መሬት ስጦታ ውል የሚደረግበት ፎርም በተመለከተ መሠታዊ የሆነ ልዩነት ያላቸው በመሆኑ ነው፡፡

በመሠረቱ አንድ ሕግ ተፈጻሚ የሚሆነው ሕጉ ሥራ ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ በሚፈጸሙ ተግባራት ላይ እንጂ ሕጉ ባልነበረበት ጊዜ ተፈጽመው ባለፉ ጉዳዮች ላይ አይደለም፡፡ አንድን አስቀድሞ የተከወነ ድርጊትን ሕጋዊነት አስመልክቶ ክርክር በተነሳ ጊዜ የድርጊቱ ሕጋዊነት ሊመረመር የሚገባውም ድርጊቱ በተከወነበት ወቅት በሥራ ላይ ያለውን ሕግ መሠረት በማድረግ እንጂ ገና ወደፊት ሊወጣ የሚችለውን ሕግ መሠረት በማድረግ አይደለም፡፡ የድርጊቱን ሕጋዊነት አስመልክቶ ክርክር የተነሳበት ጊዜም ቢሆን ይህንን የሕጉን የተፈጻሚነት መርህን ሊቀይረው አይችልም፡፡ በመሆኑም ሟች እማሆይ ጥሩ በላይ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን የገጠር መሬት ስጦታ ለአመልካች ባደረጉበት ወቅት በአማራ ክልል በሥራ ላይ የነበረው የክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 133/1998 የገጠር መሬትን አስመልክቶ የሚደረግ የስጦታ ውል በጽሑፍ እንዲደረግና መሬቱ በሚገኝበት ወረዳ ላለው የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ቀርቦ እንዲመዘገብ ከመደንገግ ባለፈ ግልጽ ኑዛዜ በሚደረግበት የውል አቀራረጽ ሥርዓት /ፎርም/ እንዲደረግ እስካልደነገገ ድረስ ከገጠር መሬት ይዞታ ልዩ ባሕሪ የተነሳ የገጠር መሬትን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ በልዩ ሁኔታ ተፈጻሚ እንዲሆን ታስቦ የወጣውን ልዩ ሕግን በመተው ጠቅላላ ሕግ የሆነውን የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎችን የገጠር መሬት ይዞታን በሚመለከቱ ክርክሮች ላይ ተፈጻሚ ማድረግም ሆነ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው የስጦታ ውል በተደረገበት ጊዜ ሳይሆን ስጦታ ሰጪዋ በሞቱበት ወቅት የወጣውን አዲሱን የገጠር መሬት አዋጅ ድንጋጌዎችን ተፈጻሚ ማድረግ የሕጎችን የተፈጻሚነት መርሕን በግልጽ የሚቃረን ነው፡፡ ምክንያቱም አንድን ክርክር በሚመለከት ልዩ ህግ እያለ ጠቅላላው ህግ በክርክሩ ላይ ተፈፃሚ እንዲደረግም ሆነ በክርክሩ ምክንያት የሆነው ድርጊት በተከሰተበት/ በተከወነበት ወቅት በሥራ ላይ ያለው ሕግ እያለ ድርጊቱ ተከስቶ ካለፈ ከዓመታት በኋላ የወጣው ሕግ ወደኋላ ተመልሶ ተፈጻሚ እንዲደረግ ዓለም አቀፋዊ ይሁንታን ያገኘው የሕጎች የተፈጻሚነት መርሕ አይፈቀደምና ነው፡፡

ስለሆነም የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የአብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ የሕጎችን የተፈጻሚነት መርሕን ያልተከተለ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ስለተገኘ ስህተቱን በማረም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ**

1. የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 0153728 በ09/02/2015 ዓ.ም እና የአብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 01-59960 ጥር 16 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በፌ/ጠ/ፍ/ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1)(ለ) መሠረት በሙሉ ድምጽ ተሽሯል፡፡

2. የባሶ ሊበን ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 0140642 በ27/05/2014 ዓ.ም እና የአብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 01-59960 ጥር 16 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ ጸንቷል፡፡
3. ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን የገጠር እርሻ መሬት ሟች እማሆይ ጥሩ በላይ በሕይወት በነበሩ ጊዜ በ13/10/1998 ዓ.ም በተደረገና በወቅቱ ለወረዳው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ቀርቦ በተመዘገበ የስጦታ ውል ለአመልካች ሰጥተው አመልካች ይዞታው በስጦታ ከተሰጣቸው ጊዜ ጀምሮ ይዞታውን በእጃቸው አድርገው ሲጠቀሙበት የቆዩት ይዞታ ስለመሆኑ በሥር ሁሉም ፍ/ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች ይዞታውን ለተጠሪ ሊለቁ አይገባም ተብሎ ተወስኗል፡፡
4. የዚህን ሰበር ክርክር ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ በውሳኔ ስለተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት እንዲመለስ ታዟል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

*የሰ/መ/ቁ 250757*
*የካቲት 26 ቀን 2017ዓ/ም*

**ዳኞች፡-** ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

ሐፊዝ አባጀማል

ማርታ ተካ

አየለ ማሞ

**አመልካቾች፡-** 1. አቢብ አብዲ
2. ቆረኔ አብዲ
3. ሰሃኔ አይዲድ
} ፀሀይ ወ/ዮሀንስ ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** 1. ዓሊ ዮሜ ዩሱፍ
2. መሐመድ ዮሜ ዩሱፍ
} አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው የገጠር መሬት ይዞታን የተመለከተ ጉዳይ ሲሆን የተጀመረው በፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪዎች ከሳሾች ሲሆኑ የአሁን አመልካቾችና ሌሎች 5 ሰዎች ተከሳሾች ነበሩ፡፡ የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ በፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 05-2-366/2014 ሕዳር 05 ቀን 2015 ዓ.ም ተሰጥቶ በየደረጃዉ ባሉት የሱማሌ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና ሰበር ችሎት የጸናዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በሚል ነዉ፡፡

**ማስታወሻ፡** - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ተጠሪዎች በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ: - ለ60 ዓመት በይዞታቸዉ ስር አድርገዉ ጫት በመትል፤ በቆሎና ማሽላ እየዘሩ ሲጠቀሙበት ነበረዉን በጅግጅጋ ከተማ አስተዳደር ቀበሌ 20 ዉስጥ የሚገኘዉን ስፋቱ 60 ቆጢ የእርሻ መሬት ይዞታቸዉን በኃይል ወረራ በማድረግ አመልካቾች ይዘዉት በፀጥታ አስከባሪዎች እንዲያቆሙ ትዕዛዝ ቢሰጣቸዉም ከድርጊታቸዉ ሳይገቱየዘሩት እህል በከፊል አዉድመዋል፡፡ ስለሆነም አመልካቾች የፈጠሩት ሁከት እንዲወገድላቸዉ እንዲወሰን የሚጠይቅ ነዉ፡፡

አመልካቾች ለቀረበባቸዉ ክስ የሰጡት መልስ ይዘት፡- ክርክር ያስነሳዉ የእርሻ መሬት አመልካቾች ነዉ፡፡ በይዞታችን ስር የሚገኝ በመሆኑ ሁከት ይወገድልን ክስ ሊቀርብብን አይችልም፡፡የእርሻ መሬቱ የ1ኛ አመልካች አባት የሆነዉ የአሊ ዩሜ ዞታ ነዉ፡፡ ተጠሪዎች በሆድለይ ቀበሌ ዉስት የራሳቸዉ የእርሻ መሬት አልነበራቸዉም፡፡ በእጃችን ለ60 ዓመት የቆየ ነዉ የሚሉት ሀሰት ነዉ በማለት የይዞታቸዉን አዋሳኞች በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡

የፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን በቃል አከራክሮ እና ሁለቱም ወገኖች በተገኙበት በይዞታዉ ላይ ምልከታ በማድረግ እና ተጠይቀዉ ከሰጡት መልስ አሊ ዮሜ መሬቱን በአደራ መልክ ይዞ እያረሰ የሚጠቀምበት መሆኑን መተማመናቸወን፤ ይዞታዉ በአሊ ዮሜና ሙሀመድ ዩሜ እጅ የሚገኝ እና አመልካቾች ሁከት መፍጠራቸዉ ተረጋግጧል በማለት አመልካቾች የተከሳሾች ይዞታ በሆነዉ ክርክር ባስነሳዉ የገጠር መሬት ይዞታ ላይ እየፈጸሙ ያሉት የሁከት ተግባር እንዲያቆሙ ወስኗል፡፡ በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝተዉ የስር ተከሳሾች ባቀረቡት ይግባኝ መነሻት ጉዳዩን የተመለከተዉ የሱማሌ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙን አከራክሮና መርምሮ ዉሳኔዉን በአብላጫ ድምጽ በማጽናት ወስኗል፡፡ በመቀጠል አመልካቾች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ያቀረቡ ቢሆንም ግራ ቀኙን አከራክሮ የስር ፍ/ቤቶችን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘት በአጭሩ፡- ተጠሪዎች ያቀረቡትን የሁከት ይወገድልኝ ክስ የማየት የዳኝነት ስልጣን የወረዳ ፍ/ቤት እንጂ የዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባለመሆኑ የፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ያለዉ በይግባኝ ሆኖ እያለ ስልጣን ሳይኖረዉ አከራክሮ መወሰኑ ስህተት ነዉ፡፡ ስር ፍ/ቤት ሁከት መኖር አለመኖሩን የሚያረጋግጥ ምንም ዓይነት ማስረጃ ሳያገኝ ሁከት ይወገድ በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ ስህተት ነዉ፡፡ የችሎቱ ዳኞች በይዞታዉ ላይ ተገኝተን ተመለከትን የሚሉት ከብዙ ጊዜያት በፊት በቦታዉ ተተክሎ የተነቀለና የደረቀ ጫት ኤን ከሚሉ በቀር ሁከት መፈጠር አለመፈጠሩን ያጣሩት ነገር በሌለበት የሰጡት ዉሳኔ ተገቢ አይደለም፡፡ ተጠሪዎች ይዞታዉ የራሳቸዉ ስለመሆኑ ያቀረቡት ማስረጃ በሌለበት ይዞታዉን እንዲለቀቅላቸዉ መወሰኑ ተገቢ ባለመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ እንዲሻር የሚጠይቅ ነዉ፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ክሱ የይዞታ መብት እንዲከበር እና ሁከት እንዲወገድ የሚል ሲሆን ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበዉ ለፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት መሆኑን መዝገቡ ያሳያል፡፡ ሁከት እንዲወገድ የሚቀርብ ክስ የመጀመሪያ ደረጃ የስረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን አስመልክቶ ሰበር በተለያዩ መዝገቦች ዉሳኔ የሰጠበት መሆኑ ይታወቃል፡፡ ስለሆነም ይዞታ መብት ላይ ሁከት እንዲወገድ በሚል የቀረበ ክስ ለመዳኘት የስረ-ነገር ስልጣን ጋር በተያያዘ እንዲሁም ስለጭብጥ አያያዝ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በተለያዩ መዛግብት ከሰጠዉ ገዥ ዉሳኔ (በሰ/መ/ቁ 86510፣ 72980፣ 102543፣ 229433 እና ሌሎች መዝገቦች) አኳያ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በሰበር ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

ተጠሪዎች ለሰበር አቤቱታዉ የሰጡት መልስ ይዘት በአጭሩ፡- ለፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪዎች ክስ ያቀረቡበት ጉዳይ የእርሻ መሬት ቢሆንም በመሬቱ ላይ ያሉት ንብረቶች የጫት ተክልን ጨምሮ ግምታቸዉ ከፍተኛ በመሆኑ የዳኝነት ስልጣኑ በከፍተኛ ፍ/ቤት ስር የሚወድቅ በመሆኑ ነዉ፡፡ ተጠሪዎች በሬቱ ላይ ያለዉን ንብረት መሠረት በማድረግ ያቀረቡትን የሁከት ይወገድልኝ ክስ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተቀብሎና አጣርቶ ሁከት ይወገድ ሲል የሰጠዉ ዉሳኔ የሚነቀፍበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ የስር ፍ/ቤት የክርክር መነሻ የሆነዉ የእርሻ መሬት የተጠሪዎች መሆኑንና በእጃቸዉ ይዘዉ እየተጠቀሙበት የሚገኙ መሆኑ በሰዉና በሰነድ ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ በተቃራኒዉ አመልካቾች በእርሻ መሬቱ ላይ ያላቸዉን መብት በማስረጃ ባማስረዳታቸዉ ሁከት እንዲወገድ የተሰጠዉ ዉሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ እንዲጸና የሚጠይቅ ነዉ፡፡

አመልካቾች ጥር 02 ቀን 2017 ዓ.ም የተዘጋጀ 2 ገጽ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸዉን በሚያጠናክር መልኩ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን እኛም አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡ የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር መርምረን እንደተረዳነዉ የዚህን ችሎት ምላሽ የሻዉ ጭብጥ፡- በሱማሌ ክልል የፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 152/2008 አንቀጽ 3(1) እና ይህ ሰበር ችሎት ከዚሁ ጋር በተያያዘ በሰ/መ/ቁ 244702፣ 229363፣ 229433፣ 244737 ከሰጣቸዉ ገዥ የሕግ ትርጉሞች አንጻር የፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የእርሻ መሬት ይዞታን አስመልክቶ ሁከት ይወገድልኝ ክስ ለመመልከት የሚያስችል የስረ-ነገር ስልጣን አለዉ ወይስ የለዉም? የሚለዉ ነዉ፡፡

ተጠሪዎች በፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ በጅግጅጋ ከተማ አስተዳደር ቀበሌ 20 ዉስጥ የሚገኝ 60 ቆጢ የእርሻ መሬት ይዞታቸዉን በረራ በመያዝ ሁከት ስለፈጠሩባቸዉ የአመልካቾች የሁከት ተግባር እንዲቆም እንዲወስንላቸዉ ሲሆን አመልካቾችን ጨምረዉ የስር ተከሳሾች ክርክር ያስነሳዉ ይዞታ

የተጠሪዎች ይዞታ ሳይሆን የአመልካቾች የራሳቸዉ ይዞታ መሆኑንና በእጃቸዉ በሚገኝ ይዞታ ላይ ሁከት ፈጠራችሁ ተብለዉ ሊከሰሱ እንደማይገባ በመግለጽ ክሱ ዉድቅ እንዲደረግላቸዉ በመጠየቅ ተከራክረዋል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራ ቀኙ በተገኙበት በይዞታዉ ላይ ምልከታ ማድረጉንና ይዞታዉ የተጠሪዎች መሆኑን እንዳመነበት በመግለጽ አመልካቾች ሁከት የፈጠሩ በመሆናቸዉ ሁከቱ እንዲቆም በማለት ወስኗል፡፡ ይህ ዉሳኔ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ሰሚ ችሎት በየደረጃዉ ጸንቷል፡፡ ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለበት አንዱና አከራካሪዉ ነጥብ የፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ ጉዳዩን አከራክሮ ለመወሰን የሚያስችለዉ የስረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን አለዉ ወይስ የለዉም? የሚለዉ ነዉ፡፡

በመሠረቱ በሶማሌ ክልል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 152/2008 አንቀጽ 3(1) ግምት የሌለዉ በሚል በተመለከተዉ መሠረት የሁከት ይወገድልኝን ክስ ተመልክቶ የመወሰን የስረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን የክልሉ ወረዳ ፍ/ቤቶች ስልጣን ስር የሚወድቅ ሲሆን የዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ደግሞ ጉዳዩን በይግባኝ ተመልክቶ የመወሰን ስልጣን ይኖረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ተመልክቶ የመወሰን ስልጣን የሌለዉ ፍ/ቤት ክስ ሲቀርብለት ወደ ክርክሩ ሂደት ከመግባቱ በፊት አስቀድሞ ጉዳዩን የማየት የስረ-ነገር ስልጣን ያለዉ መሆን አለመሆኑን መመርመር እንዳለበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 231(1/ለ) ተደንግጓል፡፡ ይህን አስመልክቶ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 244737 እና በሌሎች መዛግብት ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ተመልክቶ የመወሰን የስረ-ነገር ስልጣን የወረዳ ፍ/ቤት በሆነበት የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ተመልክቶ የሚሰጠዉ ዉሳኔ የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን ሳይኖረዉ የሰጠዉ ስለሚሆን መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን በመግለጽ አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ተጠሪዎች በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ 60 ቆጢ በሆነ የእርሻ መሬት ላይ የሁከት ተግባር በመፈጸሙ የሁከት ትግባሩና ጣልቃ ገብነቱ እንዲቆም እንዲወሰን በመሆኑ የቀረበዉክስ የሁከት ይወገድልኝ የዳኝነት ጥያቄ ነዉ፡፡ ተጠሪዎች በእርሻ መሬቱ ላይ ያለዉ ንብረት ግምቱ ከፍተኛ ስለሆነ ነዉ ለዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የቀረበዉ ቢሉም ንብረቱ ተገምቶና በግምቱ መሠረት የዳኝነት ተከፍሎበት የቀረበ የንብረት ማስመለስ ጥያቄ አይደለም፡፡ ይልቁንም የወረራና የጣልቃ ገብነት ድርጊት እንዲቆም የቀረበ የሁከት ይወገድልኝ የዳኝነት ጥያቄ ነዉ፡፡ ይህን የዳኝነት ጥያቄ በመጀመሪያ ደረጃ ተመልክቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን የወረዳ ፍ/ቤት ሆኖ እያለ የፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በሶማሌ ክልል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 152/2008 አንቀጽ 3(1) መሠረት ጉዳዩን በቀጥታ ተቀብሎ ለማየት የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን ሳይኖረዉ አከራክሮ ዉሳኔ መስጠቱን ያሳያል፡፡ ምንም እንኳ ተከራካሪዎቹ ባያነሱለትም የስር ፍ/ቤት ወደ ክርክር ሂደቱ ከመግባቱ በፊት ጉዳዩን የማየት የስረ-ነገር ስልጣን ያለዉ መሆን አለመሆኑን መመርመር ነበረበት፡፡ የፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት የስረ-ነገር ስልጣን ያለዉ መሆን አለመሆኑን ሳይመረምርና የስረ-ነገር ስልጣን ሳይኖረዉ ጉዳዩን ተመልክቶ መወሰኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 231(1/ለ)፤ በሶማሌ ክልል

ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 152/2008 አንቀጽ 3(1) ድንጋጌን፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 244737 እና በሌሎች መዛግብት የሰጠዉን አስገዳጅ ትርጉም ያላገናዘበና መሠርታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡ በየደረጃዉ ያሉት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ችሎቶች ይህንኑ ስህተት ማረም ሲገባቸዉ በፍሬ ጉዳዩ ላይ የተሰጠዉን ዉሳኔ በመመልከት ማጽናታቸዉ ተገቢ ባለመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ ሊሻርና ስህተቱ ሊታረም የሚገባዉ ነዉ፡፡

ሲጠቃለል ተጠሪዎች 60 ቆጢ የእርሻ መሬት ይዞታቸዉ ላይ ተፈጸመ ያሉት የሁከት ተግባር እንዲቆም ያቀረቡትን የሁከት ይወገድልኝ የዳኝነት ጥያቄን ተመልክቶ የመወሰን የስረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን የወረዳ ፍ/ቤት ሆኖ እያለ የፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ ተቀብሎ አከራክሮ ዉሳኔ መስጠቱም ሆነ በዉሳኔዉ ላይ የቀረበዉን ይግባኝ ዉድቅ በማድረግና ዉሳኔዉን በማጽናት በየደረጃዉ ያሉት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ችሎቶች የሰጡት ዉሳኔ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 244737 እና በሌሎች መዛግብት የሰጠዉን አስገዳጅ ትርጉም ያላገናዘበና በፌዴራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሸ) እና 10(1/ሐ) መሠረት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 05-2-366/2014 ሕዳር 05 ቀን 2015 ዓ.ም ተሰጥቶ በሶማሌ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 05-1-79/15 የካቲት 01 ቀን 2015 ዓ.ም በተሰጠ ዉሳኔ እና የክልሉ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 05-01-241/15 ግንቦት 02 ቀን 2015 ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ የጸናዉ ዉሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1/ለ) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣኑ ተመልክቶ የመወሰን የስረ-ነገር ስልጣን የለዉም ተብሎ ተወስኗል፡፡ አመልካች ጉዳዩን ለማየት የስረ-ነገር ስልጣን ላለዉ ፍ/ቤት ክስ የማቅረብ መብታቸዉን ይህ ዉሳኔ አይነካም ተብሏል፡፡
3. በዚህ መዝገብ ጥቅምት 22 ቀን 2015 ዓ.ም በፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 15/2016 የተጀመረዉ አፈጻጸም ለጊዜዉ ታግዶ እንዲቆይ የተሰጠዉ የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ዉሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት


የሰ.መ.ቁ.250942

የካቲት 27 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች፡......1. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

2. ቀነዓ ቂጣታ

3. ተሾመ ሽፈራዉ

4. ብርቅነሽ እሱባለዉ

5. ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች፡ ሲሲኢሲሲ ኢትዮጵያ ቅርንጫፍ

ተጠሪ፡ አቶ ቤልሻጽር ሀይለልዑል መ/ጽድቅ

ይህ መዝገብ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ይህ የስራ ስንብት ክርክር የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች የሥር ከሳሽ፣ የአሁን ተጠሪ የሥር ተከሳሽ ሆኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.296508 በ29/10/2015 ዓ.ም የሰጠዉ ፍርድ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት በማመልከቱ ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ የአሁን አመልካች በሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረበዉ የክስ አቤቱታ፡ አመልካች በተጠሪ ድርጅት በብሮ ስራ መሃንዲስ የሥራ መደብ ተቀጥሬ በወር 80,000 (ሰማንያ ሺህ) እየተከፈለኝ በአርሲ ሮቤ ዋቤ ሪቨር ፕሮጀክት ሲሰራ የቆየሁ ሲሆን ተጠሪ በ02/12/2014 ዓ.ም በሕገወጥ መንገድ ከሥራዬ ስላሰናበተኝ ተገቢ ክፍያዎችን እንዲከፍለኝ እንዲወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

የአሁን አመልካች በበኩሉ ባቀረበዉ መልስ ከተጠሪ ጋር የሥራ ዉል የለንም፣ ተጠሪ የተቀጠረዉ ለአርሲ ሮቤ ዋቤ ሪቨር ሮድ ፕሮጀክት ተቀጥሮ ሲሰራ የነበረና የሥራ ቅጥር ዉሉም ለዚህ ፕሮጀክት እንጂ በድርጅቱ ሥር አይደለም፣ ተጠሪ የሙከራ ጊዜ ላይ ያለ ሰራተኛ በመሆኑ ያለማስጠንቀቂያ ማሰናበቱ ተገቢ

ነዉ፣ ተጠሪ በሙከራ ጊዜ ላይ እያለ በተደጋጋሚ ከሥራ ያልፈቃድ ሲቀር ነበረ በመሆኑ ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ማሰናበቱ ሕገወጥ አይደለም፣ የተጠሪ የወር ደመወዝ ብር 70,000 (ሰባ ሺህ) የጠየቃቸዉ ክፍያዎች ተቀባይነት የላቸዉም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአሁን አመልካች የተነሳዉን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በብይን ዉድቅ በማድረግ፣ የተጠሪን የሰዉ ምስክሮችን በመስማት፣ ጉዳዩን በመመርመር በሰጠዉ ዉሳኔ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በተደረገዉ የቅጥር ዉል የተጠሪ የሙከራ ጊዜ ለሁለት ወራት የሚቆይ እንጂ ለ60 የሥራ ቀናት የሚል አይደለም፤ ከዚህ አንጻር የአሁን አመልካች ነሐሴ 2 ቀን 2014 ዓ.ም ተጠሪን ከሥራ ሲያሰናብተዉ ሁለት ወር ከ9 ቀናት በመሆኑ አመልካች ተጠሪዉን ከሥራ ያሰናበትነዉ የሙከራዉ ጊዜ ሳያበቃ ነዉ በማለት ያቀረበዉ ክርክር ተቀባይነት የለወም፡፡ አመልካች ተጠሪ ከሥራ መቅረቱን በማስረጃ ያላስረዳ በመሆኑ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ሳይሰጥ ተጠሪን ከሥራ ያሰናበተ በመሆኑ ስንብቱ ሕገወጥ ነዉ፡፡ በዚህ መሰረት የተጠሪ የተጣራ ደመወዝ ብር 78257.26 መሰረት በማድረግ የሥራ ስንብት፣ የካሳ ክፍያ፣ ተጠሪ የ14 ቀን ደመወዝ አልተከፈለኝ ይባል እንጂ በማስረጃ ስላስረዳ ተቀባይነት የለዉም፤ አመልካች ክፍያ ለዘገየበት የ3 ወር ደመወዝ በቅጣት መልክ በአጠቃላይ ብር 539391.99 ለተጠሪ እንዲከፍለዉ፣ ለጥብቅና አገልግሎት ብር ሀያ ሺህ ለተጠሪ እንዲከፍለዉ በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ የተጣራ የአሁን ተጠሪ ደመወዝ ብር 70,000 (ሰባ ሺህ) ነዉ፤ ለተጠሪ ሊከፈል የሚገባዉን የስንብት ክፍያ፣ የካሳ ክፍያ፣ ክፍያ ለዘገየበት ሶስት ወር ደመወዝ፣ የ14 ቀን ደመወዝ፣ በአጠቃላይ አመልካች ለአሁን ተጠሪ በድምሩ ብር 573,392.67 እንዲከፍለዉ በማለት የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች ሐምሌ 17 ቀን 2015 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ የአሁን ተጠሪ የሙከራ ጊዜ ሰራተኛ ሆኖ ሳለ በዚህ ጊዜ ያለማስጠንቀቂያ ማሰናበት እንደሚቻል በሕጉ ተመልክቶ እያለ የሥር ፍ/ቤት ተጠሪ የሙከራ ጊዜ ሰራተኛ አይደለም በማለት የስራ ስንብቱ ሕገወጥ ነዉ በሚል ክፍያዎችን እንዲንከፍል የወሰነዉ እንዲሸርልን፤ የሥር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የተጠሪን ደመወዝ ያስተካከለ ቢሆንም በስሌት ረገድ የድምር እንዲሁም የቀን ጭማሪ በማድረግ መወሰኑ ስህተት ስለሆን እንዲስተካከልልን፤ የአሁን ተጠሪ በእጁ ያለዉን የአመልካችን ዕቃዎች እንዲመልስ ትዕዛዝ ተሰጥቶት ባልመለሰበት ሁኔታና ግዴታዉን ሳይወጣ የሥር ፍ/ቤት አመልካች ለተጠሪ በሕጉ በተመለከተ ጊዜ ዉስጥ ክፍያን አልፈጸመም በሚል ክፍያ ለዘገየበት ቅጣት እንዲንከፍል መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲሻርልን፣ ተጠሪ ንብረቶችን እንዲያስረክብ እንዲወሰንልን በማለት በዝርዝር አመልክቷል፡፡

ይህ ሰበር ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣ የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች የአሁን ተጠሪን ከሥራ ያሰናበተዉ የሙከራ ጊዜ ካለፈ በኋላ ያለማስጠንቀቂያ በመሆኑ ስንብቱ ሕገወጥ ነዉ፣ የተጠሪ የተጣራ የወር ደመወዝ ብር 70000 (ሰባ ሺህ) ነዉ ካለ በኋላ የካሳ ክፍያ ያሳላበት አግባብ፣ ክፍያ ለዘገየበት እንዲከፈል፣ የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ተጠሪ ይግባኝ ባላቀረበበት ሁኔታ የአስራ አራት ቀን ደመወዝ የመወሰኑን አግባብነት ለማጣራት ሲባል የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ባዘዘዉ መሰረት በ18/7/2016 ዓ.ም እና በ23/03/3017 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት ባጭሩ፡ የሥር ፍ/ቤት አመልካች የሙከራ ጊዜ ካለፈ በኋላ ያለማስጠንቀቂያ ተጠሪን ከሥራ ማሰናበቱ ሕገወጥ ነዉ በማለት መወሰኑ የሚነቀፍበት የህግ መሰረት የለም፤ ክፍያ ለዘገየበት በተመለከተ አመልካች ክፍያዉን ያልፈጸመዉ ተጠሪ ሂሳብ ባለማወራረዱ ወይም የድርጅቱ ንብረት ባለመመለሱ መሆኑን በማስረጃ ያላስረደ

በመሆኑ የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ ሕግን መሰረት ያደረገ በመሆኑ ቅሬታዉ ዉድቅ ሆኖ የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ እንዲጸናልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካች ሚያዚያ 4 ቀን 2015 ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር እና ለሰበር ቅሬታዉ መነሻ ከሆኑት የሥር ፍ/ቤቶችን ዉሳኔዎች አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥና ተጨማሪ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡

በዚህ መሰረት የመጀመሪዉን ጭብጥ በተመለከተ አመልካች የአሁን ተጠሪ የሥራ ዉል በማቋረጥ ያሰናበተዉ የሙከራ ጊዜ ከማለቁ በፊት ነዉ ወይስ የሙከራ ጊዜ ካለቀ በኂላ ነዉ የሚለዉ ነጥብ ነዉ፡፡ የአሁን አመልካች ባቀረበዉ ክርክር ተጠሪ ከሥራ የተሰናበዉ በሕግ በተመለከተዉ 60 የሥራ ቀናት የሙከራ ጊዜ ከማለቁ በፊት በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 11 (5) መሰረት ስንብቱ ሕጋዊ ነዉ የሚል ሲሆን፣ የአሁን ተጠሪ በበኩሉ አመልካች የሥራ ዉሉን በማቋረጥ ያሰናበተኝ የሙከራ ጊዜ ካለቀ በኂላ በመሆኑ ስንብቱ ሕገወጥ ነዉ በማለት ተከራክሯል፡፡ በዚህ ረገዳ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠዉ ፍሬ ነገር ሲታይ አመልካች እና ተጠሪ ግንቦት 23 ቀን 2014 ዓ.ም ያደረጉት የቅጥር ዉል ላይ ተጠሪ ለሙከራ ጊዜ የተቀጠረ መሆኑን የሚያመለክት ሲሆን፣ የሙከራ ጊዜ ቆይታዉ ደግሞ ለሁለት ወራት መሆኑን እንደሚያመለክት ነዉ፡፡ በሌላ በኩል አመልካች የተጠሪን የሥራ ዉል በማቋረጥ ከሥራ ያሰናበተዉ ነሐሴ 2 ቀን 2014 ዓ.ም መሆኑን በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ እንግዲህ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በተደረገዉ የቅጥር ዉል የተጠሪ የሙከራ ጊዜ የሚቆየዉ ለሁለት ወር መሆኑን በግልጽ እስከተመለከተ ድረስ ፍ/ቤት ግልጽ ከሆነዉ የዉሉ ድንጋጌ በመራቅ ሁለት ወር የሚለዉ የሥራ ቀናትን ብቻ የሚያመለክት ወይም የሚያጠቃለል ነዉ ብሎ መተርጎም የሚችሉበት ሁኔታ የለም፡፡ እንደሚታወቀዉ የሙከራ ጊዜዉ ሰራተኛዉ ስራ ከጀመረበት ቀን አንስቶ 60 የሥራ ቀናት ሊበልጥ እንደማይችል በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 11 (3) ድንጋጌ ሥር ተመልክቷል፡፡ የሙከራ ጊዜ ላይ ያለ ሰራተኛ ለሥራዉ ተስማም አለመሆኑ ሲረጋገጥ አሠሪዉ ማስጠንቀቂያ መስጠት ሳይጠበቅበት፣ የሥራ ስንብት ክፍያና ካሳ መክፈልም ሳይገደድ የሥራ ዉሉን ሊያቋርጥ እንደሚችል በዚህ ሕግ አንቀጽ 11 (5) ሥር ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንጻር አሁን የተያዘዉ ጉዳይ ሲታይ ግራ ቀኙ ያደረጉት የሙከራ ጊዜ ለሁለት ወር የሚቆይ ከሆነ ለሰራተኛዉ በአዋጁ ከተመለከተዉ በተሻለ ሁኔታ የሚጠቅም የሥራ ቅጥር ዉል ያደረጉ መሆኑን ስለሚያመለክት፣ ፍ/ቤቱ ከዉሉ ግልጽ ቃል በመራቅ ሁለት ወር ማለት የሥራ ቀናትን ብቻ የሚመለከት ነዉ በሚል የሚተረጎምበት የህግ አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም ግራ ቀኙ የሙከራ ጊዜዉ ለተከታታይ ለሁለት ወር የሚቆይ መሆኑን እስከተስማሙ ድረስ፣ ሰራተኛዉ ሥራዉን ከጀመረበት ቀን ጀምሮ ሁለት ወር ከመቁጠር ዉጭ ይህ ጊዜ የስራ ቀናትን ብቻ የሚመለከት ተብሎ የሚተረጎምበት አግባብ የለም፡፡ በዚህ መሰረት ተጠሪ ግንቦት 23 ቀን 2014 ዓ.ም ተቀጥሮ ሥራዉን ከጀመረበት ቀን አንስቶ በአመልካች ከሥራዉ እስከተሰናበተበት ነሐሴ 2 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ ሲቆጠር ሁለት ወር ከ9 ቀናት መሆኑን የሥር ፍ/ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጠዉ ጉዳይ ነዉ፡፡ በሌላ በኩል አመልካች ያነሳዉ ክርክር ተጠሪ ከሥራ ሊሰናበት የቻለዉ ለ10 ተከታታይ የሥራ ቀናት ከሥራ በመቅረቱ ነዉ የሚል ሲሆን ተጠሪ ይህን ፍሬ ነገር ክዶ ተከራክሯል፡፡ በዚህ ረገድ የሥር ፍ/ቤት ባደረገዉ ማጣራት አመልካች ተጠሪ ለ10 ተከታታይ የሥራ ቀናት ከሥራዉ የቀረ መሆኑን በማስረጃ ያላስረዳ መሆኑን ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ አመልካች የአሁን ተጠሪ ለ10 ተከታታይ የሥራ ቀናት ከሥራ መቅረቱን ባላስረዳበት ሁኔታ የሥራ ዉሉን በማቋረጥ ተጠሪን ከሥራዉ ያሰናበተዉ የሙከራ ጊዜዉ ካለቀ በኂላ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች ፍሬ ነገር የማጣራትና ማስረጃን መርምሮና መዝኖ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ዉሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

በሕግ በተሰጣቸዉ ስልጣን መሰረት አመልካች የአሁን ተጠሪን ከስራዉ ያሰናበተዉ የሙከራ ጊዜዉ ካለቀ በኋላ በሕገወጥ መንገድ በመሆኑ ስንብቱ ሕገወጥ በሚል የደረሰበትን ድምዳሜ ይህ ሰበር ችሎት በሕግ ከተሰጠዉ ስልጣን አንጻር የሚቀበለዉ የፍሬ ነገር ድምዳሜ ነዉ ከሚባል በቀር መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚያስችል ነገር አልተገኘም፡፡

ሁለተኛዉን ጭብጥ በተመለከተ የተጠሪ የወር ደመወዝ ብር 70,000 (ሰባ ሺህ) መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ የካሳ ክፍያ የተሰላበትን አግባብነት የሚመለከት ነዉ፡፡ ከዚህ አንጻር በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠዉ ፍሬ ነገር ሲታይ የተጣራ የወር ደመወዝ ብር 70,000 (ሰባ ሺህ) መሆኑን ያሳያል፡፡ የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ግን ያለምንም ማስረጃ የተጠሪ የወር ደመወዝ ብር 78,267.28 ነዉ በሚል የካሳ ክፍያ ያሰላ ቢሆንም የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህን በማረም የተጠሪ የወር ደመወዝ ብር 70000 (ሰባ ሺህ) መሆኑን በማመልከት አመልካች ለተጠሪ መክፈል የሚገባዉን አመልካች ተጠሪዉን ከሥራዉ ባያሰናብተዉ ያገኝ የነበረዉ ደመወዝ የሶስት ወር ከ21 ቀን በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 43 (4) (ለ) መሰረት የካሳ ክፍያ ብር 259,000 (ሁለት መቶ አምሳ ዘጠኝ ሺህ) እንዲከፍለዉ መወሰነዉን የዉሳኔዉ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ በመሆኑም የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት የተጠሪ የተጣራ የወር ደመወዝ ብር ሰባ ሺህ መሆኑን በማረጋገጥ በዚህ አግባብ የካሳ ክፍያ ተሰልቶ ለተጠሪ እንዲከፈል መወሰኑ የሚነቀፍበት የህግ አግባብ የለም፡፡

ሶስተኛዉን ጭብጥ በተመለከተ አመልካች ለተጠሪ በሕግ በተመለከተ የጊዜ ገደብ ዉስጥ ክፍያ ያልፈጸመ በመሆኑ፣ ክፍያ ለዘገየበት የሶስት ወር ደመወዝ በቅጣት መልክ ለተጠሪ እንዲከፍል የተወሰነዉ በሕጉ አግባብ መሆን አለመሆኑን የሚመለከት ነዉ፡፡ እንደሚታወቀዉ የሥራ ዉል ሲቋረጥ የሰራተኛዉ ደመወዝና ከዉሉ መቋረጥ ጋር የተያያዙ ክፍያዎች ሁሉ በሰባት የሥራ ቀናት ዉስጥ መከፈል እንዳለባቸዉ፣ ይህ ጊዜ ሊራዘም የሚችለዉ ሠራተኛዉ ከአሠሪዉ የተረከበዉን ንብረት ባለማስረከቡ ወይም የሚፈለግበትን ሂሳብ ባለማወራረዱ በራሱ ጥፋት የዘገየ እንደሆነ መሆኑን በአንቀጽ 36 ደንጋጌ ሥር ተመልክቶ እናገኛለን፡፡ አሠሪዉ በዚህ ድንጋጌ ሥር በተመለከተዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥ ለሠራተኛዉ ክፍያዉን መክፈል ያለበት ሠራተኛዉ የጠየቀዉ ክፍያ አለመግባባት ወይም ክርክር ያልተነሳበት እና በአሠሪዉ የታመነ መሆን እንደሚገባዉ ከአዋጁ አንቀጽ 37 ይዘትና ዓላማ የሚንረዳዉ ጉዳይ ነዉ፡፡ ሠራተኛዉ የጠየቀዉ ክፍያ ክርክር የሌለበት እና በአሠሪዉ የታመነ ሆኖ ሳለ፣ አሠሪዉ በዚህ የጊዜ ገደብ ዉስጥ ለሰራተኛዉ ክፍያዉን ያልፈጸመዉ እንደሆነ በአንቀጽ 38 መሰረት ክፍያዉ ለዘገየበት ጊዜ አሠሪዉ ለሰራተኛዉ እስከ ሶስት ወር የሚደርስ ደመወዝ በቅጣት መልክ እንዲከፍለዉ የሥራ ክርክር ችሎት መወሰን እንደሚችል ያስገነዝባል፡፡ በዚህ አግባብ አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመመርመር ተጠሪ የ14 ቀን ደመወዝ አልተከፈለኝም ይበል እንጂ ይህ ደመወዝ ያልተከፈለዉ መሆኑን በማስረጃ ያላስረዳ መሆኑንና አመልካች በበኩሉ ለተጠሪ ደመወዝ የከፈለዉና ቀሪ ክፍያ የሌለ መሆኑን በማስረጃ ያስረዳ ስለሆነ በዚህ ረገድ የተጠሪ ጥያቄ ተቀባይነት የለዉም በማለት መወሰኑን የዉሳኔዉ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ ስለሆነም አመልካች ለተጠሪ መክፍል የሚገባዉና ያመነ ክፍያ መኖሩን የሚያመለክት ነገር የለም፡፡ ከዚህም በላይ የአሁን ተጠሪ በሥራዉ ምክንያት እጁ የገባዉን የአመልካች ንብረት በመመለስ ክሊራንስ በመዉሰድ ክፍያዉ እንዲፈጸምለት መጠየቁን የሚያሳይ ነገር የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች ለተጠሪ መክፈል የሚገባዉና ያመና ክፍያ ካለመኖሩም በላይ ለተጠሪ ያልተከፈለ ቀሪ የወር ደመወዝ ክፍያ እንደሌለ በማስረጃ ተረጋግጦ ባለበት እንዲሁም ተጠሪ የአመልካች ንብረት መመለሱን ክሊራንስ ማቅረቡን የሚያመለክት ነገር በሌለበት፣ የሥር ፍ/ቤት ክፍያ ለዘገየበት የሶስት ወር ደመወዝ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል በማለት መወሰኑ ከፍ ሲል የተጠቀሰዉን የአዋጁን ድንጋጌ የሚቃረን በመሆኑ የሕግ መሰረት የለዉም፡፡

አራተኛዉን ጭብጥ በተመለከተ አመልካች ለተጠሪ ያልተከፈለዉን የ14 ቀን ደመወዝ እንዲከፍለዉ በሚል በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠዉ ዉሳኔ አግባብነትን የሚመለከት ነዉ፡፡ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰዉ የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመመርመር ተጠሪ የ14 ቀን ደመወዝ አልተከፈለኝም ይበል እንጂ ይህ ደመወዝ ያልተከፈለዉ መሆኑን በማስረጃ ያላስረዳ በመሆኑንና አመልካች በበኩሉ ለተጠሪ ደመወዝ የከፈለዉና ቀሪ ክፍያ የሌለ መሆኑን በማስረጃ ያስረዳ ስለሆነ በዚህ ረገድ የተጠሪ ጥያቄ ተቀባይነት የለዉም በማለት መወሰኑን የዉሳኔዉ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ በዚህ ረገድ የአሁን ተጠሪ በራሱ በኩል ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበዉ ቅሬታ መኖሩን የሚያመለክት ነገር የለም፡፡ በመሆኑም የአሁን ተጠሪ የ14 ቀን ደመወዝ አልተከፈለኝም በሚል የጠየቀዉ ዳኝነት በሥር ፍ/ቤት ዉድቅ መደረጉን በመቃወም ቅሬታዉን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ በዚህ ረገድ ባልተከራከሩበት ሁኔታ አመልካች ለተጠሪ ያልተከፈለዉን የ14 ቀን ደመወዝ ሊከፍለዉ ይገባል በሚል የወሰነዉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.320 (1)፣ 327 እና ተከታዮቹን ድንጋጌዎች የሚቃረን በመሆኑ የህግ ድጋፍ የለዉም፡፡ በመሆኑም በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ጉዳይ የሰጡት ዉሳኔ የሚነቀፍ ነዉ ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤት የአሁን አመልካች የተጠሪን የስራ ዉል በማቋረጥ ከሥራ ያሰናበተዉ የሙከራ ጊዜ ካለቀ በኋላ በሕገወጥ መንገድ መሆኑን በማረጋገጥ ስንብቱ ሕገወጥ በሚል ተገቢ ሆኑ ክፍያዎች ለተጠሪ እንዲከፈል መወሰኑ ተገቢ ቢሆንም ክፍያ ለዘገየበት የሶስት ወር ደመወዝ እና የ14 ቀን ደመወዝ ለተጠሪ እንዲከፈል የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ዉሳኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.186656 ሚያዚያ 05 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.296508 በ29/10/2015 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9 (1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች የካሳ ክፍያ ብር 259,000 (ሁለት መቶ አምሳ ዘጠን ሺህ) እና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ብር 70,000 (ሰባ ሺህ) ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል ብለናል፡፡
3. አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል በሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት የተወሰነዉ የሥራ ስንብት ክፍያ አልተነካም ጸንቷል፡፡
4. የአሁን አመልካች ክፍያ የዘገየበት የሶስት ወር ደመወዝ በቅጣት መልክ እና የ14 ቀናት ደመወዝ ለተጠሪ ሊከፍለዉ አይገባም ብለናል፡፡
5. ግራ ቀኙ የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

## ትዕዛዝ

- የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
- ይህ ሰበር ችሎት በ30/11/2015 ዓ.ም የሰጠዉ እግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
- ይህ ዉሳኔ በ10/7/2017 ዓ.ም ተነቧል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ፋ/ዘ**

**ማስታወሻ፡** - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት


የሰ/መ/ቁ 252056

የካቲት 25 ቀን 2017ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ

ሽመክት አሰፋ

በዕዉቀት በላይ

መላኩ ካሳዬ

አየለ ማሞ

አመልካች፡- አቶ ኃይለ ጊዮርግስ ይልማ ወልደአብ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ አዲስ እሸቱ - ጠበቃ መሳይ ተድላ - ቀረቡ

2. አቶ መስፍን ገ/ማሪያም -

3. ወ/ሪት ኤደን አክሊለ

4. ወ/ሮ ሰላማዊት መኮንን - ጠበቃ መዓዛ ክብረት

መዝገቡ የተቀጠረዉ የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ ተገቢዉን ለመስራት ሲሆን ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ይህ የሰበር መዝገብ ተከፍቶ ለዚህ ሰበር ችሎት የቀረበዉ የአብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 123279 ሰኔ 15 ቀን 2015 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን ገልጾዉ አመልካች በ03/12/2015 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸዉ ነዉ፡፡


**ማስታወሻ፡** - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ለዚህ የሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነዉ ክርክር የተጀመረዉ በአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን ጣርማ በር ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን በወረዳዉ ፍርድ ቤት 1ኛ ተጠሪ ከሳሽ የአመልካች አዉራሽ ሟች አቶ ይልማ ወልደአብና ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ 1ኛ ተጠሪ በጣርማ በር ወረዳ ፍርድ ቤት ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተራ ቁጥር ላይ በተጠቀሱት ተጠሪዎችና በአመልካች አባት በሟች አቶ ይልማ ወልደአብ ላይ ባቀረቡት ክስ በክሱ ላይ አዋሳኞቹ የተመለከተዉን 400 ካሬ ሜትር ላይ ያረፈዉን  የመኖሪያ ቤት ከነሰርቪስ  ቤቶቹ ጭምር የካቲት 27 ቀን 2011 ዓ/ም በተፈረመ የሽያጭ ዉል ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተጠሪዎች (ከሥር 1ኛ እስከ 3ኛ ተከሳሾች) በብር 200,000 (ሁለት መቶ ሺህ) ገዝተዉ ካርታ በስማቸዉ የተሰጣቸዉ ቢሆንም በይዞታዉ ላይ ካሉ ቤቶች መካከል አንዱን የአመልካች ወላጅ አባት (የሥር 4ኛ ተከሳሽ) ይዘዉ ለመልቀቅ ፈቃደኛ አለመሆናቸዉን ገልፀዉ ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተጠሪዎች (የሥር 1ኛ እስከ 3ኛ ተከሳሾች) የሸጡላቸዉን ቤት ከአመልካች አባት (የሥር 4ኛ ተከሳሽ) አስለቅቀዉ እንዲያስረክቡና የአመልካች አባትም (የሥር 4ኛ ተከሳሽም) መብት ሳይኖራቸዉ የያዙትን የ1ኛ ተጠሪን (የሥር ከሳሽን) ቤት ለቀዉ እንዲወጡ እንዲወሰንላቸዉ ዳኝነት በመጠየቅ ክስ አቅርበዋል፡፡

ለዚህ የ1ኛ ተጠሪ ክስ የሥር 1ኛ እስከ 3ኛ ተከሳሾች የነበሩት የአሁን ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተጠሪዎች እና የሥር 4ኛ ተከሳሽ የነበሩት የአመልካች አባት መልስ እንዲሰጡ በፍ/ቤቱ ታዘዉ ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተጠሪዎች በ1ኛ ተጠሪ የክስ ማመልከቻ ላይ የተጠቀሰዉን በ400 ካሬ ሜትር ይዞታ ላይ የተሠራዉን ቤት ከአዉራሻቸዉ ከወ/ሮ እሸቴ ወዳጆ በዉርስ አግኝተዉና ስመ ሀብቱን ወደ ስማቸዉ አዛዉረዉ ለ1ኛ ተጠሪ መሸጣቸዉንና የአመልካች አባት (የሥር 4ኛ ተከሳሽ) በይዞታዉ ላይ ከሚገኙ ቤቶች መካከል አንዱን በጉልበት ይዘዉ እንደሚገኙ ገልፀዉ እንደ ክሱ አቀራረብ ቢወሰን ተቃዉሞ እንደሌላቸዉ በመግለጽ መልስ የሰጡ ሲሆን 4ኛ ተከሳሽ የነበሩት የአመልካች አባት በበኩላቸዉ ለቀዉ እንዲወጡ ዳኝነት ተጠይቆባቸዉ የተከሰሱበትን ቤት ሟች ወ/ሮ እሸቴ ወዳጆ ፈቅደዉላቸዉ በ1984 ዓ/ም በግል ገንዘባቸዉ የሠሩትና ሟቿ በሕይወት በነበሩበት ጊዜም ራሳቸዉ ተከሳሹ ሲጠቀሙበት የቆዩት የግል ሀብታቸዉ እንጂ የወ/ሮ እሸቴ ወዳጆ ሀብት ባለመሆኑ ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተጠሪዎች (የሥር 1ኛ እስከ 3ኛ ተከሳሾች) የአዉራሻቸዉ ንብረት ያልሆነዉን ቤት ከአዉራሻቸዉ ሀብት ጋር ቀላቅለዉ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በስማቸዉ አዉጥተዉ በሽያጭ ለሥር ከሳሽ (ለ1ኛ ተጠሪ) ሊሸጡ የሚችሉበት የሕግ አግባብ እንደሌለ ገልፀዉ የግል ሀብታቸዉ የሆነዉን ቤት ለማስለቀቅ የቀረበዉ ክስ ዉድቅ ተደርጎ ከሳሽ የሽያጭ ዉሉን የሟቿ ሀብት በሆነዉ ቤትና ይዞታ ላይ ብቻ እንዲያስፈጽሙ እንዲወሰንላቸዉ በመጠየቅ ክሱን ሙሉ በሙሉ ክደዉ ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ በኃላ የወረዳዉ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን እያከራከረ ያለዉ ቤት በሟች ወ/ሮ እሸቴ ወዳጆ ስም ተመዝግቦ በሚገኘዉ ይዞታ ላይ የተሠራና የሟች ወ/ሮ እሸቴ ወዳጆ ሕጋዊ ወራሾች ለከሳሽ (ለአሁን 1ኛ ተጠሪ) መሸጣቸዉን ያረጋገጡት ቤት ስለሆነ የሥር 4ኛ ተከሳሽ የነበሩት የአመልካች አባት ቤቱን ለቀዉ እንዲወጡና የሥር 1ኛ እስከ 3ኛ ተከሳሾችም (የአሁን ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተጠሪዎች) ባመኑት መሠረት ቤቱን ለከሳሽ (ለአሁን 1ኛ ተጠሪ) እንዲያስረክቡ የወሰነ ሲሆን ይህ ዉሳኔ እስከ አብክመ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ

ችሎት ድረስ ደርሶ በመጽናቱና ክርክሩ በሂደት ላይ እያለ የአመልካች አባት ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸዉ አመልካች በዉሳኔዉ ላይ የሰበር አቤቱታ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበዉ ሰበር ሰሚዉ ችሎት ግራ ቀኙን አከራክሮ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ የክርክሩን ቤት የሠሩት የአመልካች ወላጅ አባት መሆን አለመሆናቸዉ፣ ሠርተዉ ከሆነ የሠሩት በሟች ወ/ሮ እሸቴ ወዳጆ ፈቃድ መሆን አለመሆኑ፣ ቤቱን የሠሩት የአመልካች አባት ከሆኑና የሠሩትም በሟች ወ/ሮ እሸቴ ወዳጆ ፈቃድ ከሆነ ግንባታዉን ተፈቅዶላቸዉ መሥራታቸዉ በግኙ ዉል ይዞታዉን ካገኙት ገኙ አንጻር በገነቡት ቤት ላይ የሚያጎናጽፋቸዉ መብት መኖር አለመኖሩና ተያያዥ ጭብጦች በወረዳዉ ፍ/ቤት እንደገና ተጣርተዉ እንዲወሰኑ በመወሰን ጉዳዩን ወደ ጣርማ በር ወረዳ ፍ/ቤት መልሶታል፡፡

ከዚህ በኋላ የወረዳዉ ፍ/ቤት ጉዳዩን በግራ ቀኙ ማስረጃ ካጣራ በኋላ የአመልካች አባት ለቀዉ እንዲወጡ የተከሰሱበትን ቤት ራሳቸዉ የሠሩ ስለመሆኑ፣ ቤቱን የሠሩትም ሟች ወ/ሮ እሸቴ ወዳጆ ፈቅደዉላቸዉ እንደሆነና እስከ ሟች ወ/ሮ እሸቴ ወዳጆ ሕልፈተ ሕይወት ድረስም ሆነ ከዚያ በኋላ ክርክሩ እስከተጀመረበት ጊዜ ድረስ የክርክሩ ቤትና ቤቱ ያረፈበት ይዞታ ከነጓሮዉ ጭምር ከሟች ወ/ሮ እሸቴ ወዳጆ ቤት በአጥር ተለይቶ በአመልካች ወላጅ አባት በሟች አቶ ይልማ ወልደአብ እጅና ኋላ ላይም በአመልካች እጅ የነበረ ስለመሆኑ በማስረጃ እንደተረጋገጠ ገልጾ የአመልካች ወላጅ አባት በገንዘባቸዉ የሠሩት ቤት ባለቤትና ባለይዞታዋ ፈቅደዉ የሰጡት የቤቱ ጓሮ ባለመብት ስለሆኑ ሟቿ በሕይወት እያሉ የአመልካች አባት ሲጠቀሙበት የነበረዉን ቤትና የቤቱን ጓሮ ይዞታ አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ ሊያስረክቡ እንደማይገባ ገልጾ የ1ኛ ተጠሪን ክስ ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

ከዚህ በኋላ 1ኛ ተጠሪ በዚህ የጣርማ በር ወረዳ ፍርድ ቤት ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ይግባኝ ሰሚዉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መልስ ሰጭዎችን አስቀርቦ ግራ ቀኙን በማከራከር ይግባኙን በመዝገብ ቁጥር 0138556 መርምሮ የክርክሩ ቤት የአመልካች ወላጅ አባት ሟች አቶ ይልማ ወልደአብ በሟች ወ/ሮ እሸቴ ወዳጆ ይዞታ ላይ በፈቃዳቸዉ የሠሩት ቤት ስለመሆኑ በማስረጃ መረጋገጡን፣ በባለ መሬቱ ፈቃድ በሌላ ሰዉ መሬት ላይ ቤት የሠራ ሰዉ የቤቱ ባለቤት እንደሚሆን የፍ/ሕ/ቁጥር 1179 የሚደነግግ በመሆኑ የክርክሩ ቤት የአመልካች አባት ንብረት (ሀብት) እንጂ የሟች ወ/ሮ እሸቴ ወዳጆ ሀብት እንዳይደለ፣ ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተጠሪዎች ሊወርሱና በሽያጭ ለሌላ ሰዉ ሊያስተላልፉ የሚችሉት የአዉራሻቸዉ የሟች ወ/ሮ እሸቴ ወዳጆ ሀብት የሆነዉን ብቻ እንጂ የአመልካች አባት የሟች አቶ ይልማ ወልደአብ ሀብት የሆነዉን የክርክሩን ቤት ጭምር አለመሆኑን፣ በመሆኑም ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተጠሪዎች የአዉራሻቸዉ ሀብት ያልሆነዉን የክርክሩን ቤት ስመ ሀብት ጭምር ወደ ራሳቸዉ ስም በማዛወር የያዙት የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ አግባብነት በሌለዉ መንገድ የተሰጣቸዉ በመሆኑ በክርክሩ ቤት ላይ መብት ሊያስገኝላቸዉ እንደማይችልና ይህንን መብት የማያስገኝላቸዉን ሰነድ መሠረት በማድረግ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር የፈጸሙት የሽያጭ ዉልም የክርክሩን ቤት በተመለከተ ለ1ኛ ተጠሪ መብት እንደማያስገኝላቸዉ ገልጾ ይግባኙን ዉድቅ በማድረግ የጣርማ በር ወረዳ ፍ/ቤትን ዉሳኔ አጽንቷል፡፡

ይህም በመሆኑ 1ኛ ተጠሪ የጣርማ በር ወረዳ ፍ/ቤትና የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት ለአብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበለትን የሰበር አቤቱታ መርምሮ በአቤቱታዉ ላይ በተጠሪነት የተጠቀሱትን አመልካችንና የአሁን ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተጠሪዎችን አስቀርቦ ካከራከራቸዉ በኋላ ምንም እንኳ የክርክሩ ቤት በሟች ወ/ሮ እሸቴ ወዳጆ ይዞታ ላይ በፈቃዳቸዉ የተሠራ መሆኑ በማስረጃ ቢረጋገጥምና ከዚህም የተነሳ በፍ/ሕ/ቁጥር 1179(1) መሠረት የአመልካች አባት የሟች አቶ ይልማ ወልደአብ ሀብት ቢሆንም በፍ/ሕ/ቁጥር 1179(2) ላይ እንደተደነገገዉ በመሬቱ ላይ ሌላ ሰዉ ቤት እንዲሠራ የፈቀደዉ ባለ መሬት የቤቱን ግምት ከፍሎ ቤቱን ለራሱ ለማስቀረት ስለሚችልና ቤቱን የሠራዉ ሰዉ ግምቱን ለመቀበል ፈቃደኛ ካልሆነ ቤቱን አፍርሶ መሬቱን መልቀቅ ያለበት በመሆኑ አመልካች የቤቱን ግምት ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተጠሪዎች ላይ መጠየቅ አሊያም ቤቱን አፍርሰዉ ይዞታዉን መልቀቅ ከሚኖርባቸዉ በቀር ቤቱንና ይዞታዉን ላለመልቀቅ ሊከራከሩና የቤቱንም ግምት የቅን ልቦና ገዥ ከሆኑት 1ኛ ተጠሪ ላይ ሊጠይቁ እንደማይችሉ ገልጾ የጣርማ በር ወረዳ ፍ/ቤትንና የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ዉሳኔ ሽሮታል፡፡

በመሆኑም አመልካች ይህ የአብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ትርጉም ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን ገልጸዉ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስለመሆኑ በአቤቱታቸዉ ላይ ያነሱት ዋና የቅሬታ ነጥብ የክርክሩ ቤት ቤቱ የተሠራበት ይዞታ ባለመብት የነበሩት ሟች ወ/ሮ እሸቴ ወዳጆ ፈቅደዉ በአመልካች ወላጅ አባት በሟች አቶ ይልማ ወልደአብ የተሠራ ስለመሆኑ ተረጋግጦ እያለ፣ በባለ ይዞታዉ ፈቃድ በሌላ ሰዉ ይዞታ ላይ ቤት የሠራ ሰዉ የቤቱ ባለሀብት (ባለቤት) ስለሆነ ግምቱ ተከፍሎት ቤቱን እንዲለቅ አሊያም ቤቱን አፍርሶ ከይዞታዉ ላይ እንዲያነሳ ሊጠየቅ እንደማይችል የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 36638፣ በሰ/መ/ቁጥር 105125 እና በሌሎችም መዝገቦች አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶ እያለና 1ኛ ተጠሪም ከክርክሩ ቤት በ100 ሜትር ርቀት ላይ የሚኖሩና ቤቱ በአመልካች ወላጅ አባት በሟች አቶ ይልማ ወልደአብ የተሠራ ስለመሆኑ በሚገባ እያወቁ ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተጠሪዎች ተገቢ ባልሆነ መንገድ አሠርተዉ የያዙትን ይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ መሠረት በማድረግ ግዥ መፈጸማቸዉ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 60720 በሰጠዉ አስገዳጅ ዉሳኔ መሠረት የቅን ልቦና ገዥ የማያስብላቸዉ ሆኖ እያለ 1ኛ ተጠሪ የቅን ልቦና ገዥ እንደሆኑና አመልካች ቤቱን ለቀዉ ለ1ኛ ተጠሪ ካስረከቡ በኋላ የቤቱን ግምት ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተጠሪዎች ላይ እንዲጠይቁ ተገልጾ መወሰኑ አስገዳጅ የሰበር ዉሳኔዎችን ጭምር የሚቃረን መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን የሚገልጽ ነዉ፡፡

ይህ የአመልካች የሰበር አቤቱታ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ተመርምሮ የክርክሩ ቤት የአመልካች አባት በባለይዞታዋ ፈቃድ የሠሩት ቤት ስለመሆኑ ተረጋግጦ እያለ አመልካች ቤቱን እንዲለቁ የተወሰነበት አግባብ በሰ/መ/ቁጥር 36638፣ በሰ/መ/ቁጥር 105125 እና በሌሎችም መዝገቦች ከተሰጠዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉምና

በኢ/ፌ/ዲ/ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40(3) ላይ ከተረጋገጠዉ የንብረት መብት አኳያ በሰበር ሰሚዉ ችሎት ሊታይ የሚገባ መሆኑ ተገልጾ ተጠሪዎች ለአቤቱታዉ መልስ እንዲሰጡ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡

በዚህም መሠረት ተጠሪዎች ቀርበዉ በተለያዩ ቀናት በየግላቸዉ ጽፈዉ ባቀረቡት ተመሳሳይ ይዘት ባለዉ መልስ ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተጠሪዎች የሟች ወ/ሮ እሸቴ ወዳጆ ወራሾች መሆናቸዉን አረጋግጠዉና የክርክሩን ቤት ጨምሮ በ400 ካሬ ሜትር ይዞታ ላይ የተሠራዉ የመኖሪያ ቤት ከነሰርቪሶቹ ጭምር በዉርስ ሀብትነት አጣርተዉ ስመ ሀብቱን ወደ ስማቸዉ በማዛወር የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ በስማቸዉ አሠርተዉ ቤቱን ለ1ኛ ተጠሪ የሸጡ በመሆኑ አመልካች የሽያጭ ዉሉን ሊቃወሙ እንደማይችሉና የሚቃወሙ ቢሆን እንኳ መብታቸዉን ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተጠሪዎች ላይ ሊጠይቁ ከሚገባ በቀር አግባብ ካለዉ አካል የተሰጠዉን የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ተመልክተዉ ቤቱን በቅን ልቦና ከገዙት 1ኛ ተጠሪ ላይ ሊጠይቁ እንደማይገባ ገልጸዉ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ እንዲጸናላቸዉ በመጠየቅ መልስ ሰጥተዋል፡፡ የሰበር አመልካችም የሰበር ቅሬታቸዉን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ አጠር ተደርጎ የተገለጸዉ ሲሆን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር አቤቱታዉ ለሰበር ሰሚዉ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ (የማስቀረቢያ ነጥብ) እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡

እንደመረመረዉም ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉ ቤት የአመልካች ወላጅ አባት ሟች አቶ ይልማ ወልደአብ በባለ ይዞታዋ በሟች ወ/ሮ እሸቴ ወዳጆ ፈቃድ በ1984 ዓ/ም የሠሩት፣ ከዚያን ጊዜ ጀምሮም እስከ ዕለተ ሞታቸዉ ድረስ ሲኖሩበት የነበረና እሳቸዉ ከሞቱ በኋላም እስከ አሁን ድረስ አመልካች ይዘዉ የሚኖሩበት ቤት ስለመሆኑ በማስረጃ ስለመረጋገጡ ከጣርማ በር ወረዳ ፍ/ቤት ጀምሮ እስከ አብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ በየደረጃዉ ያሉ የክልሉ ፍ/ቤቶች በተስማማ አኳኋን የተቀበሉት ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ ይህ ከተረጋገጠ ደግሞ ቤቱ የሟች አቶ ይልማ ወልደአብ ሀብት ስለመሆኑ ክርክር የማይቀርብበት ጉዳይ ሲሆን ይህ ቤት በአሁኑ ጊዜ በሥራ ላይ ካለዉ የመንግሥት የመሬት ፖሊሲ አኳያ ባለ ይዞታዋ የነበሩት ሟች ወ/ሮ እሸቴ ወዳጆም ሆኑ የሟቿ ሕጋዊ ወራሾች የሆኑት ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተጠሪዎች ግምት ከፍለዉ ሊያስለቅቁ የሚችሉት ሳይሆን ባለሀብትነታቸዉ በማናቸዉም አግባብ ቢሆን ሊነካ የማይቻል የሟች አቶ ይልማ ወልደአብ የግል ሀብታቸዉ ነዉ፡፡ በመሆኑም ቤቱ ምንም እንኳ የአመልካች ወላጅ አባት የሟች አቶ ይልማ ወልደአብ ሀብት ቢሆንም ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተጠሪዎችና አዉራሻቸዉ የሆኑት ሟች ወ/ሮ እሸቴ ወዳጆ ግምቱን ለአመልካች ወላጅ አባት ለሟች አቶ ይልማ ወልደአብ ወይም ለአመልካች ከፍለዉ ሊያስለቅቁ የሚችሉት ቤት እንደሆነ ተገልጾ የተሰጠዉ የአብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ የኢ/ፌ/ዲ/ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40(3) ድንጋጌንና በዚህ ረገድ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 36638፣ በሰ/መ/ቁጥር 105125 እና በሌሎችም መዝገቦች የሰጠዉን አስገዳጅ የሰበር ዉሳኔ የሚቃረን ነዉ፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች በዚህ ረገድ ያቀረቡት ክርክር የሕግ መሠረት ያለዉ ሆኖ አልተገኘም፡፡

አመልካች መብታቸዉን መጠየቅ ያለባቸዉ በቅን ልቦና ቤቱን ከገዙት ከ1ኛ ተጠሪ ላይ ሳይሆን ቤቱን ለ1ኛ ተጠሪ ከሸጡት ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተጠሪዎች እንደሆነ ተገልጾ የተሰጠዉን የክልሉን ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔንና ይህንን ዉሳኔ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎች ያቀረቡትን ክርክር በተመለከተ በርግጥ የአንድ ጠንቃቃ ገዥ መብት ሊከበርና ሕጋዊ ጥበቃም ሊደረግለት የሚገባ ስለመሆኑ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በበርካታ መዝገቦች አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የተሰጠበትን ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡ ነገር ግን እነዚህ ዉሳኔዎች ተፈጻሚነት የሚኖራቸዉ ገዥዉ የቅን ልቦና ገዥ መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነዉ፡፡ ምክንያቱም በመርህ ደረጃ አንድ ሰዉ ለራሱ የሌለዉን የንብረት መብት ለሌላ ሰዉ ሊያስተላልፍ የማይችል በመሆኑ ሻጩ የሚሸጠዉ ንብረት ትክክለኛ ባለሀብት ስለመሆኑ ተገቢዉን ጥንቃቄ ሳያደርግ የገዛ ገዥ ንብረቱን በግዥ ያገኘ መሆኑን ብቻ ምክንያት በማድረግ በንብረቱ ላይ ሻጩ ያልነበረዉን መብት ሊያገኝ ስለማይችል ነዉ፡፡ በዚህ ረገድም ገዥ በሻጭ ስም የተሰጠዉን የባለሀብትነት ማስረጃን እንደ ብቸኛ መከራከሪያ አድርጎ ሊያቀርብ አይችልም፡፡ በርግጥ በፍ/ሕ/ቁጥር 1195 ላይ እንደተደነገገዉ በአንድ ሰዉ ስም አግባብ ካለዉ አካል የተሰጠ የባለሀብትነት ማስረጃ ማስረጃዉ የተሰጠዉ ሰዉ የንብረቱ ባለሀብት ስለመሆኑ ግምት የሚያስወስድ ነዉ፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ግምት በሌላ አሳማኝ ማስረጃ ሊስተባበል የሚችል በመሆኑ ማስረጃዉን የያዘዉ ሰዉ የንብረቱ ባለሀብት አለመሆኑን እያወቀ ግዥዉን የፈጸመዉ ሰዉ የባለሀብትነት ማረጋገጫ ሰነዱን እንደ መከራከሪያ አድርጎ ሊያቀርብ አይችልም፡፡

አሁን በተያዘዉ ጉዳይ የክርክሩ ቤት የአመልካች ወላጅ አባት ሟች አቶ ይልማ ወልደአብ በባለይዞታዋ በሟች ወ/ሮ እሸቴ ወዳጆ ፈቃድ የሠሩት ቤት ስለመሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ ሲሆን ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተጠሪዎች ይህንን የአዉራሻቸዉ ሀብት ያልሆነዉን ቤት ከሟቿ በዉርስ ከሚያገኙት ሌላ ቤት ጋር በመቀላቀል ሀብትነቱን ወደ ስማቸዉ ማዛወራቸዉ ሕገወጥ ተግባር እንጂ በማናቸዉም አግባብ መብት የሚያስገኝላቸዉ አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ 1ኛ ተጠሪ የክርክሩ ቤት ሲሠራ ጀምሮ ከቤቱ በ100 (አንድ መቶ) ሜትር ርቀት ላይ ነዋሪ ሆነዉ ቤቱ በማን እንደተሠራ ጠንቅቀዉ ያዉቁ የነበረ ስለመሆኑ በአመልካች የቀረበዉን ክርክር ሁሉም ተጠሪዎች አስተባብለዉ አልተከራከሩም፡፡ በመሆኑም ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተጠሪዎች የቤቱን ስመ ሀብት ወደ ራሳቸዉ ሲያዛወሩትም ሆነ 1ኛ ተጠሪ ቤቱን ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተጠሪዎች ላይ ሲገዙ ቤቱ የ2ኛ እስከ 4ኛ ተጠሪዎች አዉራሽ የሟች ወ/ሮ እሸቴ ወዳጆ ንብረት ሳይሆን የአመልካች ወላጅ አባት የሟች አቶ ይልማ ወልደአብ ንብረት መሆኑን እያወቁ በመሆኑ ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተጠሪዎች አግባብነት በሌለዉ መንገድ በስማቸዉ ያወጡት የባለሀብትነት ማስረጃ በአመልካች ላይ መከራከሪያ ሆኖ ሊቀርብባቸዉ አይችልም፡፡ በዚህ ረገድም በሕገወጥ መንገድ የተሰጠ የባለሀብትነት ማስረጃ አንዳችም መብት የማያስገኝ ስለመሆኑና የባለሀብነት ማስረጃዉ አግባብ ባልሆነ መንገድ የተገኘ መሆኑን እያወቀ ይህንን ማስረጃ መሠረት በማድረግ በአከራካሪዉ ንብረት ላይ መብት ያገኘ ሰዉም ይህንን ማስረጃ በትክክለኛዉ ባለሀብት ላይ በመከራከሪያነት ሊያቀርብ የማይችል ስለመሆኑ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 60720 (ቅጽ 11) እና በሌሎችም መዝገቦች አስገዳጅ ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡

ስለሆነም የአብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ የኢ/ፌ/ዲ/ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40(3) ድንጋጌንም ሆነ በተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 36638፣ በሰ/መ/ቁጥር 105125፣ በሰ/መ/ቁጥር 60720 እና በሌሎችም መዝገቦች የሰጠዉን አስገዳጅ የሰበር ዉሳኔን የሚቃረን መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ስለተገኘ

ስህተቱን በማረም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል።

## <u>ዉሳኔ</u>

1. የአብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 123279 ሰኔ 15 ቀን 2015 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በፌ/ጠ/ፍ/ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1)(ለ) መሠረት በሙሉ ድምጽ ተሽሯል።

2. የጣርማ በር ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 0120263/12 በ4/9/2014 ዓ/ም እና የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 0138556 በ25/2/2015 ዓ/ም የሰጡት ዉሳኔ ጸንቷል።

3. ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉ ቤት ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተጠሪዎች አዉራሽ ሟች ወ/ሮ እሸቴ ወዳጆ በፈቀዱት መሠረት የአመልካች ወላጅ አባት ሟች አቶ ይልማ ወልደአብ የሠሩትና 1ኛ ተጠሪም በክርክሩ ቤት 100 ሜትር ርቀት ላይ ሆነዉ እዉነቱን እያወቁ ቤቱን ከ2ኛ እስከ 4ኛ ተጠሪዎች የገዙ ስለመሆኑ ከአመልካች የቀረበዉን ክርክር በግልጽ ያላስተባበሉ ስለሆነ ቤቱ አመልካች ከሟች አባታቸዉ የሚወርሱት የግል ሀብታቸዉ ስለሆነ አመልካች ቤቱን ለ1ኛ ተጠሪ ሊለቁ አይገባም ተብሎ ተወስኗል።

4. የዚህን ሰበር ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል። መዝገቡ በዉሳኔ ስለተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት እንዲመለስ ታዟል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ፋ/ዘ

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ.መ.ቁ.252953

የካቲት 26 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች፡……1. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

2. እንዳሻዉ አዳነ

3. ቀነዓ ቂጣታ

4. ተሾመ ሽፈራዉ

5. ብርቅነሽ እሱባለዉ

አመልካች፡ ……..የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የቀረበ የለም

ተጠሪ፡……………አቶ መጣልኝ መላኩ የቀረበ የለም

ይህ መዝገብ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ይህ የ40/60 የመኖሪያ ቤት ክርክር የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች የሥር 1ኛ ተከሳሽ፣ የአሁን ተጠሪ የሥር ከሳሽ፣ በዚህ ሰበር ችሎት የክርክሩ ተሳታፊ የሆኑት የከተማ መሰረተ ልማት ሚኒስቴር፣ የአዲስ አበባ ቁጠባ ቤቶች፣ የአዲስ አበባ ቤቶች ኮርፖሬሽን፣ እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥር 2ኛ-5ኛ ተከሳሾች ሆኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.306150 በ17/11/2015 ዓ.ም የሰጠዉ ብይን መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት በማመልከቱ ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ ከሳሽ (የአሁን ተጠሪ) በሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረበዉ የክስ አቤቱታ፡ ከሳሽ በ2005 ዓ.ም የ40/60 የመኖሪያ ቤት መርሃ ግብር ተመዝግቤ በአሁኑ ወቅቱ ባጠቃላይ 430000 ማለትም መቶ ፐርሰንት የቆጠብኩኝ በመሆኑ በዉሉና በመመሪያዉ መሰረት ቅድሚያ ዕጣ እንዲወጣልኝ

መደረግ ሲገባዉ ከመመሪያዉ ዉጭ አርባ ፐርሰንት የቆጠቡ ሰዎች ተካተዉ እጣ እንዲወጣ በመደረጉ መብቴን አጣቧል፡፡ ከሳሽ ከ1ኛ ተከሳሽ ጋር ባደረግነዉ ዉል ቤቱን ሊያስገኝ የሚያስችል ዉል የተዋዋልንና ግዴታዬን የተወጣሁ ቢሆንም ሌሎች ተከሳሾችም በመመሪያ ቁጥር 21/2005 መሰረት የሚጠበቅባቸዉን አስተዳደራዊ ኃላፊነታቸዉን በመወጣት ቤቱን ሊያስረክቡኝ አልቻሉም፡፡ 1ኛ ተከሳሽ ከ3ኛ ተከሳሽ ጋር ባደረገዉ ሰነድ መሰረት ተገንብተዉ የተጠናቀቁትን ቤቶች ከቢሮዉ ተረክቦ በዉሉ መሰረት ቅድሚያ ማስረከብ ሲገባዉ ይህን ያላደረገ በመሆኑ፣ ሌሎች ተከሳሾችም ኃላፊነታቸዉን ያልተወጡ በመሆናቸዉ፣ በመመሪያዉና በዉሉ መሰረት ተገንብተዉ ከተጠናቀቁ ቤቶች ላይ ከአንዱ ሳይት እንዲወስድ ተከሳሾች በአንድነትና በነጠላ ኃላፊነት አለባቸዉ ተብሎ እንዲወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

1ኛ ተከሳሽ (የአሁን አመልካች) በዚህ ክስ ላይ ባቀረበዉ መልስ ከሳሽ ባቀረበዉ ክስ ከተከሳሽ ጋር ቤት ሊያስገኝ የሚችል ዉል ተዋዉለናል ይበል እንጂ በከሳሽ እና በ1ኛ ተከሳሽ መካከል ነሐሴ 7 ቀን 2005 ዓ.ም የተፈረመዉ ‹‹የመኖሪያ ቤት መግዣ የቁጠባ ዉል›› ከሳሽ የጠቀሰዉን ድንጋጌ አላስቀመጣም፤ በከሳሽ እና በ1ኛ ተከሳሽ መካከል የተደረገዉ ዉል የተፈጸሚነቱ ጊዜ አብቅቷል፡፡ ዉሉም የመኖሪያ ቤት መግዣ የቁጠባ ዉል እንጂ ቤት ሰርቶ ለከሳሽ የማስረከብ ዉል አይደለም፡፡ ከሳሽ ከሌሎች ተከሳሾች በዚህ መልክ በጣምራ የገባዉ ዉል የለም፡፡ የ40/60 የመኖሪያ ቤት ልማት ለሁሉም ቤት ፈላጊዎች የተዘጋጃ እንጂ ለከሳሽ በግላቸዉ የተሰራላቸዉ ቤት የለም፤ የ1ኛ ተከሳሽ ግዴታ የሚጀመረዉ ቤት ሰርቶ የሚያስረክበዉ አካል ቤቱን ሲያስረክበዉ መረከብ እንጂ አስረክቡኝ ብሎ መጠየቅ የለበትም፣ የተረከበዉም ቤት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡ ሌሎች ተከሳሾችም የከሳሽ ክስ ተቀባይነት የለዉም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተከሳሾች የተነሳዉን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በብይን ዉድቅ በማድረግ፣ በፍሬ ጉዳይ በሰጠዉ ዉሳኔ የ40/60 የጋራ መኖሪያ ቤት መርሃ ግብር በተመለከተ በመመሪያ ቁጥር 21/2005 አንቀጽ 16 መሰረት መቶ ፐርሰንት ለቆጠቡ ደንበኞች ቅድሚያ እንዲያገኙ መብት የሚሰጥ በመሆኑ፣ ከሳሽ ባለሁለት መኝት 40/60 የመኖሪያ ቤት ተመዝግበዉ 100% የቆጠቡ ስለሆነ፣ ከሳሽ ከ1ኛ ተከሳሽ ጋር ነሐሴ 7 ቀን 2005 ዓ.ም የመኖሪያ ቤት መግዣ የቁጠባ ዉል ስምምነት ያደረገዉ በመሆኑ፣ በዉሉ አንቀጽ 1 መሰረት 1ኛ ተከሳሽ የአዲስ አበባ ቁጠባ ቤቶች ልማት ኢንተርፕራይዝ የሚያቀርበዉን ቤት በባንኩ 100% ለቆጠቡ ደንበኞች የዉል ግዴታ የገባ በመሆኑ፣ በመመሪያ አንቀጽ 16 (2) መሰረት እጣ የሚወጣዉ ቅድሚያ ከከፍተኛ ወደ ዝቅተኛ እንደቀደም ተከተላቸዉ መሆን እንዳለበት ስለሚያመለክት፣ 1ኛ ተከሳሽ በመመሪያዉ መሰረት ከአዲስ አበባ ቤቶች ልማት ኢንተርፕራይዝ ጋር በገባዉ የመግባቢያ ሰነድ ስምምነት መሰረት ለከሳሽ 40/60 የጋራ መኖሪያ ባለ2 መኝታ ቤት ሊያስረክብ ይገባል፤ 1ኛ ተከሳሽ በቀጠይም በመመሪያዉ እጣ በመዉጣት በዉሉ መሰረት ቤቱን እንዲያስክብ፤ 2ኛ እና 4ኛ ተከሳሾች ለከሳሽ የሚያስረክቡት ቤት የለም በማለት ወስኗል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበለትን ይግባኝ በብይን ዉድቅ በማድረግ የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች ነሐሴ 30 ቀን 2015 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ የአሁን ተጠሪ የአዲስ አበባ ቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ ያወጣዉ መመሪያ ቁጥር 03/2011 አንቀጽ 41 መሰረት በዚህ ጉዳይ ለሥር ፍ/ቤት ቀጥታ ክስ ለማቅረብ አይችልም፣ የሥር ፍ/ቤቱም ይህን ጉዳይ ለማየት ስልጣን የለዉም፡፡ አመልካች ከተጠሪ ጋር ያደረገዉ ዉል ለተጠሪ ቤቱን ለማስረከብ በቅድሚያ ቤቱን ከሚመለከተዉ አካል መረከብ እንዳለበት እና ዉሉ በዚህ የቅድመ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ መሆኑን የሥር ፍ/ቤት በዉሳኔዉ አመልክቶ እያለ፣ በሚመለከተዉ አካል ቤቶቹ ተገንብቶ የተረከበዉ መሆኑን ባልተረጋገጠበት፣ አመልካች ቤቱን አስረክቡኝ ብሎ መጠየቅ የማይችል በመሆኑ፣ አመልካች ለቤት እድለኞች ብድር የማቅረብ እንጂ ሌላ ስልጣንም ሆነ መብት በቤቶቹ ላይ የሌለዉ ሆኖ ሳለ፣ የሥር ፍ/ቤቶች ተጠሪ 100% የቆጠበ በመሆኑ አመልካች በተጠሪ ጥያቄ መሰረት ቤቶቹ ላይ እጣ በማዉጣት ቤቱን ለተጠሪ እንዲያስረክበዉ በሚል ያሳለፉት ዉሳኔ መመሪያ ቁጥር 21/2005፣ ዉሉን እና መመሪያ ቁጥር 03/2011 የሚቃረንና መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲሻርልን በማለት አመልክቷል፡፡

ይህ ሰበር ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣ተጠሪ ለ40/60 የጋራ መኖሪያ ቤት 100% በመቆጠባቸዉ አመልካች ያለ እጣ ለተጠሪ ቅድሚያ ለመስጠት የሚያስገድደዉ ኃላፊነት ያለዉ መሆኑን አለመሆኑን ከዉላቸዉ፣ ከመመሪያ ቁጥር 21/2005 እና መመሪያ ቁጥር 03/2011 አንጻር ለማጣራት ሲባል የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ባዘዘዉ መሰረት በ28/10/2016 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት ባጭሩ፡ ተጠሪ የ40/60 የጋራ መኖሪያ ቤት ተመዝግቦ ዉል ሲዋዋል ተፈጻሚነት የነበረዉ የፍትሐ ብሔር ሕጉ እና መመሪያ ቁጥር 21/2005 ዓ.ም በመሆኑ አመልካች ባቀረበዉ ቅሬታ መመሪያ ቁጥር 3/2011 በመጥቀስ የሥር ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለዉም በማለት ያቀረበዉ አቤቱታ ተቀባይነት የለዉም፡፡ የአመልካች ባንክ ድርሻ ቁጠባ ሂሳብ መሰብሰብ ቢሆንም ባደረገዉ ዉል መሰረት ቤቶችን ከሚመለከተዉ አካል ተረክቦ እጣ በመዉጣት የማስተላለፍ ግዴታ ያለበት በመሆኑ፣ አመልካች ይህን ስልጣኑን ለሌላ አካል አሳልፎ በመስጠት ዉሉ በቅድመ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ነዉ ቤቱን ገንብቶ የሚያስረክብ ሳይኖር ቤት ከየት አመጣለሁ በማለት ያቀረበዉ ክርክር ተቀባይነት የለዉም፡፡ የመመሪያ ቁጥር 21/2005 እና መመሪያ ቁጥር 3/2011 በአንድ ላይ ተፈጻሚ ሊሆኑ አይችሉም፤ የአሁን ተጠሪ ከአመልካች ጋር ያደረገዉ ዉል ባልተፈጸመበት መመሪያ መለወጡ የተጠሪን መብትና ጥቅም የሚጎዳ ነዉ፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ ከዉልም ሆነ ከሕግ አንጻር የሚነቀፍ ባለመሆኑ ዉሳኔዉ እንዲጸናልኝ በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካች ሐምሌ 15 ቀን 2016 ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር እና ለሰበር ቅሬታዉ መነሻ የሆነዉን የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በዘረጋዉ የቤት ልማት ፕሮግራም መሰረት የአሁን ተጠሪ

የ40/60 ቤት ልማት ፕሮግራም ዉስጥ ለባለሁለት መኝታ የጋራ መኖሪያ ቤት በ2005 ዓ.ም ተመዝግበዉ ለቤቱ ግዢ የሚለዉን ገንዘብ መቶ ፐርሰንት በአመልካች ባንክ መቆጠባቸዉ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ የአሁን ተጠሪ ባቀረበዉ ክስ በዚህ የቤት ልማት ፕሮግራም ቤቱን በቅድሚያ ለማግኘት የሚያስችለኝን ገንዘብ መቶ ፐርሰንት ስለቆጠብኩኝ አመልካች በገባዉ ዉል መሰረት ተገንብተዉ ከተጠናቀቁ ቤቶች ላይ ከአንዱ ሳይት እንዲወስድ እንዲወሰንልኝ የሚል ዳኝነት የጠየቀ ሲሆን፣ አመልካች በበኩሉ ባቀረበዉ ክርክር ከተጠሪ ጋር ያደረግነዉ ዉል አመልካች ከሚመለከተዉ አካል ያልተረከበዉን ቤት ለማስረከብ ግዴታ የማይጥል በመሆኑ ክሱ ተቀባይነት የለዉም በማለት ተከራክሯል፡፡

እንደሚታወቀዉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአስተዳደሩ ተገንብተዉ ለተጠቃሚዎች እንዲተላለፉ የሚወስናቸዉን 10/90፣ 20/80፣ 40/60 የጋር መኖሪያ ቤቶች የቤት ልማት ፕሮግራም ተግባራ ያደረገ መሆኑን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ ካወጣዉ የቤት ፈላጊዎች የምዝገባ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 21/2005 እና የጋራ መኖሪያና ንግድ ቤቶች ለተጠቃሚዎች ለማስተላለፍ የወጣ መመሪያ ቁጥር 3/2011 ይዘትና ዓላማ መረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ መመሪያ መረዳት እንደሚቻለዉ በዚህ የቤት ልማት ፕሮግራም መሰረት ቤቶችን የሚገነባቸዉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ መሆኑን፤ ግንባታቸዉ ተጠናቀዉ ለተጠቃሚዎች የሚተላለፉ ቤቶችን መረጃ ማጣራትና የማደረጀት፣ ቤቶቹን ለተጠቃሚዎች ለማስተላለፍ ብቁ መሆናቸዉን የማረጋገጥና የመጠቀሚያ ፈቃድ የመስጠት ኃላፊነት ያለበት የሚመለከተዉ የከተማ አስተዳደር መሆኑን፤ ቤቶቹ ለተጠቃሚዎች ለመተላለፍ የቅድሚያ ክፍያ በመመሪያዉ መሰረት ባንክ የተቆጠበ መሆኑንና ሌሎች አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸዉ የሚያረጋግጠዉ የሚመለከተዉ የከተማዉ አስተዳደር አካል መሆኑን፣ ለተጠቃሚዎች ለመተላለፍ ዝግጁ የሆኑትን ቤቶች በተመለከተ መረጃ ማጣራትና ለዕጣ ለማዘጋጀት ከሚያስፈልጉት ጉዳዮች ዉስጥ አንዱ የቤት ፈላጊዉ በገባዉ ግዴታ መሰረት የቁጠባ መጠን በአመልካች ባንክ በትክክል ተቀማጭ ያደረገ መሆኑን ማረጋግጥና የቆጣቢዎችን መረጃ ከአመልካች ባንክ በየጊዜዉ የሚመለከተዉ የከተማዉ አስተዳደር የሚረከብ ስለመሆኑ፤ በመመሪያዉ የተጠቀሱትን ቅድመ ሁኔታዎችን የሚያሟሉትን የቤት ፈላጊ ተመዝጋቢዎች እጣ የሚያወጣ የሚመለከተዉ የከተማ አስተዳደር መሆኑን፤ እጣ የደረሳቸዉን የቤት እድለኞች በጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣና ለሚመለከተዉ አካላት ሁሉ እንዲሰራጭ የሚያደርገዉ የሚመለከተዉ የከተማዉ አስተዳደር አካል መሆኑን፤ የቤት እድለኛዉ የአመልካች ባንክ በመላክ የሚጠበቅባቸዉን የቅድሚያ ክፍያ ወይም ሙሉ ክፍያ መፈጸማቸዉን የሚያረጋግጠዉ የሚመለከተዉ የከተማዉ አስተዳደር አካል መሆኑን፤ የሚመለከተዉ የከተማዉ አስተዳደር አካል የቤት ሽያጭ ዉል ከቤት እድለኛዉ ጋር በመዋዋል የቤቱን ካርታ በማዘጋጀት ከአመልካች ባንክ ጋር በተፈረመዉ የመግባቢያ ሰነድ ስምምነት መሰረት የቤት እድለኞች ከአመልካች ባንክ የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ የብድር ትስስር የሚፈጥርላቸዉ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ከዚህ መመሪያ መገንዘብ የሚቻለዉ የአመልካች ባንክ ሚና በቤት ልማት ፕሮግራሙ አስፈላጊዉን ሁኔታዎች አሟልተዉ ተመዝግበዉ፣ የሚጠበቅባቸዉን ሁሉ ፈጽመዉ

እጣ የወጣላቸዉን የቤት እድለኞች የቁጠባ ሂሳብ ከፍተዉ የቅድሚያ ክፍያ እንዲቆጥቡ እና ከፍ ሲል በተጠቀሰዉ አግባብ በሚመለከተዉ የከተማዉ አስተዳደር አካል እጣ ወጥቶለት የቤት ሽያጭ ዉል ፈጽመዉ ካርታ ተሰርቶላቸዉ የብድር አገልግሎት ከአመልካች ባንክ እንዲያገኙ ባንኩ ቤቶቹን በመያዣነት በመያዝ ቤቱ የተገዛበትን ዋጋ ቀሪ ክፍያ የሚከፍሉበትን ልዩ የቁጠባ ሂሳብ በማስከፈት ክፍያ እንዲፈጽሙ ማድረግ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ከዚህ ዉጭ የአመልካች ባንክ በቤት ልማት ፕሮግራሙ መሰረት ቤት የመገንባት፣ በመመሪያዉ መሰረት አስፈላጊዉን ቅድመ ሁኔታዎችን ለሚያሟሉት የቤት ፈላጊዎች እጣ የማዉጣት እና የቤት እድለኞችን በመለየት ቤቱን ለቤቱ እድለኞች የማስረከብ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን አያመለክትም፡፡

በመሰረቱ የአመልካች ባንክ የፋይናንስ ተቋም እንደመሆኑ መጠን የተቋቋመበት ዓላማ በፋይናንስ ዘርፍ የባንክ አገልግሎትና ተያያዥነት ያላቸዉን የፋይናንስ አገለግሎት መስጠት እንጂ ቤት ገንብቶ የማስረከብ አለመሆኑን የሚታወቅ ጉዳይ ነዉ፡፡ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ነሐሴ 7 ቀን 2005 ዓ.ም የተደረገዉ ዉል ‹‹የመኖሪያ ቤት መግዣ የቁጠባ ዉል›› መሆኑን እንጂ ‹‹የመኖሪያ ቤት ገንብቶ የማስረከብ ዉል›› መሆኑን አያመለክትም፡፡ ከዚህ መረዳት እንደሚቻለዉ የአመልካች ባንክ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በዘረጋዉ የቤት ልማት ፕሮግራም መሰረት በመመሪያዉ የተቀመጡትን ቅድመ ሁኔታዎች አሟልተዉ ተመዝግበዉ እና በመጨረሻም እጣ ወጥቶላቸዉ የቤት እድለኞች ለሆኑት የቅድሚያ ክፍያ ወይም ሙሉ ክፍያ ለመቆጥብ የሚያስችላቸዉን ልዩ የቁጠባ ሂሳብ መክፈትና ገንዘብ መቆጠብ እንዲችሉ ማድረግ፣ የቤቱን የመግዣ ሙሉ ዋጋ ላልከፈሉት የቤት እድለኞች የብድር አገልግሎት በማመቻቸት ቤቱን በመያዣ በመያዝ ለከተማዉ አስተዳደር አካል የቤቱን መግዣ ዋጋ በመክፈል፣ የቤት እድለኞች ደግሞ ቀሪዉን ዋጋ ለባንኩ እንዲከፍሉ ልዩ የቁጠባ ሂሳብ በማስከፈት እንዲከፍሉ ማድረግ እንጂ ቤቶችን ገንብቶ ለቤት ፈላጊዎች ማስተላለፍ አለመሆኑን ያመለክታል፡፡ ግራ ቀኞቸዉ ያደረጉት የመኖሪያ ቤት መግዣ የቁጠባ ዉል ለግንኙነታቸዉ ግዢ ሕግ መሆኑን ከፍ/ብ/ሕ/ቁ.1731 (1) ድንጋጌ የሚገነዘበዉ ጉዳይ ነዉ፡፡ የግራ ቀኙ መብትና ግዴታ የሚነጫዉ ከዚህ ዉል እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ አመልካች በዉልም ሆነ በመመሪያ ያልተጣለበትን ግዴታ ለተጠሪ ለመፈጸም የሚገደድበት የሕግ አግባብ አይኖርም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ግንባታቸዉ ተጠናቆ ለተጠቃሚያዎች የሚተላለፉ ቤቶችን የእጣ አወጣጥ ሂደትን በተመለከተ አመልካች በዉልም ሆነ በሕግ የተጣለበት ኃላፊነት በሌለበት፣ ከእጣ አወጣጥ ቅደም ተከተል ጋር በተያያዘ አመልካች እጣዉ በመመሪያዉ መሰረት እንዲወጣ በማድረግ ቤቱን መቶ ፐርሰንት ለቆጠቡ ተመዝጋቢዎች እንዲያስረክብ በማለት ያሳለፈዉ ዉሳኔ የዉልም የህግም መሰረት የሌለዉ በመሆኑ ተቀባይነት የለዉም፡፡ በመሆኑም አመልካች በዉሉ መሰረት ቤት ገንብቶ ለተጠሪ ለማስረከብ የገባዉ ግዴታ በሌለበት እና በተጠቀሰዉ ከመመሪያና አግባብነት ካለዉ የሕግ ድንጋጌ አንጻር ቤት ገንብቶ የማስረከብ ግዴታ ሳይኖርበት፣ የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች በመመሪያዉ መሰረት ከአዲስ አበባ ቤቶች ልማት ኢንተርፕራይዝ ጋር በገባዉ የመግባቢያ ሰነድ ስምምነት መሰረት ለተጠሪ 40/60 የጋራ መኖሪያ ባለሁለት መኝታ ቤት ሊያስረክብ ይገባል፤ አመልካች በቀጠይም በመመሪያዉ እጣ በመዉጣት

በዉሉ መሰረት ቤቱን መቶ ፐርሰንት ለቆጠበዉ ሰዉ እንዲያስረክብ በሚል የሰጠዉ ዉሳኔ የዉልም ሆነ የሕግ ድጋፍ የሌለዉ በመሆኑ ተቀባይነት የለዉም፡፡ የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት በበኩሉ ይህን ዉሳኔ ማረም ሲገባዉ በብይን ማጽናቱ የሕግ መሰረት የለዉም ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች ለተጠሪ ቤት ገንብቶ ለማስረከብ የገባዉ ግዴታ በሌለበት ቤት እንዲያስረክበዉ በማለት ያሳለፉት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ዉሳኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.302611 በ25/5/2015 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.306150 በ17/11/2015 ዓ.ም የሰጠዉ ብይን መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የአሁን አመልካች በሚመለከተዉ የከተማዉ አስተዳደር አካል ተጠሪ የቤት እድለኛ መሆኑ ተረጋግጦ የቤት ሽያጭ ዉል በማድረግ እንዲረከብ ያልተወሰነዉን ቤት ለተጠሪ የማስረከብ ግዴታ የለበትም ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኙ የሰበር ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

## ትዕዛዝ

- የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመ**

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት


የሰ/መ/ቁ 253783

የካቲት 27 ቀን 2017 ዓ/ም

**ዳኞች፡-** ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻዉ አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ብርቅነሽ እሱባለው

**አመልካች፡-** ኤልያስ ዳሪ ቀርበዋል

**ተጠሪዎች፡-** 1. ወ/ሮ ሰናይት አብርሃ ቀርበዋል

2. አቶ አስመሮም ሚካኤል

3. አቶ ሽሩይ ሚካኤል

4. ወ/ሪት ራሔል ሚካኤል

5. አቶ ዮሴፍ ሚካኤል — 5ኛ ተጠሪ 4ኛ እና 6ኛ ተጠሪዎች ጭምር

6. አቶ አለምሰገድ ሚካኤል — ቀርበዋል በመወከል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የሽያጭ ውል ይፈጸምልኝ ክስ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በተጀመረበት በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ባቀረቡት ክስ 1ኛ ተጠሪ ሚስትና የወራሽ ወኪል ሆነው ከ3ኛ-6ኛ ያሉት


**ማስታወሻ፡** - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

ተጠሪዎች ጋር በጋራ በመሆን በድሮ ቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 3 የይዞታ መለያ ቁጥር AA000040301555 የሆነ በ348 ካ.ሜ ላይ ያለውን ቤትና ይዞታቸውን ጥቅምት 24 ቀን 2011 ዓ/ም በተደረገ የሽያጭ ውል በብር 2,900,000 ሽጠውልኝ በዚህ ውል መሰረት ለሻጮች በየድርሻቸው መጠን እንዲካፈሉት በቼክ ለሁሉም ግማሽ ክፍያው የተከፈላቸው ሲሆን በሽያጭ ውሉ መሰረት ውሉ በተደረገ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የሽያጭ ውሉ ፎርማሊቲውን አሟልተው ውሉን በሰነዶች ምዝገባ ጽ/ቤት ቀርበው ሲያስመዘግቡና ቤትና ይዞታውን ከቤቱ አስረጂ ሰነድ ጋር ሲያስረክቡኝ ቀሪውን ገንዘብ ልከፍላቸው የተስማማን ሲሆን ተጠሪዎች በውሉ መሰረት እንዲፈጽሙ በተደጋጋሚ ብጠይቅም 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ፍቃደኛ ሲሆኑ ከ3ኛ እስከ 6ኛ ያሉ ተጠሪዎች ግን ፍቃደኛ ባለመሆናቸው ተጠሪዎች በውሉ የተጠቀሰውን ቤት ከነይዞታው ቤቱን ከሚመለከቱ ሰነዶች ጭምር እንዲያስረክቡኝ እንዲወሰንልኝ፤ እንዲሁም የቤቱን ስመሀብት ከሻጮች ወደ ገዢ ለማስተላለፍ የሚያስፈልጉ ፎርማሊቲዎችን እንዲያሟሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች የሽየጭ ውሉን ከቀሪዎቹ ተጠሪዎች ጋር ማድረጋቸውን በማመን መልስ የሰጡ ሲሆን ከ3ኛ እስከ 6ኛ ያሉት ተጠሪዎች በሰጡት የፍሬ ነገር መልስ አመልካች ባቀረቡት ረቂቅ ውል ላይ የጋራ ባለሀብት የሆኑት 3ኛ ተጠሪ አልፈረሙም፡፡ ከ3ኛ እስከ 6ኛ ከተመለከቱት ተጠሪዎች ጋር በሕግ የተቀመጠው መስፈርት ሁሉ ተሟልቶ በውል አዋዋይ ፊት የተፈረመ ውል የለም፡፡ የሽያጭ ሂደቱ በጅምር ሊቀር የቻለው አንድም 1ኛ ተጠሪ ከሽያጭ ዋጋው ላይ ብር 600,000 ለራሳቸው በማስቀረታቸው እና አመልካች የሽያጩን ዋጋ እንዲከፍል ሲጠየቅ ክፍያውን ፈጽሞ ሂደቱን ለማጠናቀቅ ፈቃደኛ ሳይሆን በመቅረቱ ነው፡፡ ከ4ኛ እስከ 6ኛ የተመለከቱት ተጠሪዎችም ፈቃድ ቢሆን የተገኘው የእነዚህን ተጠሪዎች መንፈስ ቀላልነት ልምድ እና በዘርፉ እውቀት የሌላቸው መሆኑን እንደመልካም አጋጣሚ በመጠቀም ነው፡፡ 3ኛ ተጠሪ ከሽያጩ የተቀበለው የቼክ ክፍያ የለም፡፡ በአጠቃላይ የአመልካች ክስ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የስር የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር እና ማስረጃ ሰምቶ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ውል መኖሩን ማመናቸዉን፤ ከ3ኛ ተጠሪ ውጭ ያሉት ተጠሪዎች የሽያጭ ውሉ አለመኖሩን ክደው ያልተከራከሩ መሆኑን፤ 3ኛ ተጠሪም በውሉ አልፈረምኩም በሚል ክደው ቢከራከሩም ውሉ ላይ ፊርማቸው ያለና ግማሽ የሽያጭ ገንዘብ በድርሻቸው በቼክ የተከፈላቸው መሆኑን፤ ሌሎች ተጠሪዎችም ቢሆን በውክልናቸውና በራሳቸው በመቅረብ በሽያጭ ውሉ ላይ የፈረሙ እና በውሉ መሰረት ገንዘቡን በየድርሻቸው የተከፈላቸው ስለመሆኑ በቀረበው የሰውና የሰነድ ማስረጃ የተረጋገጠ መሆኑን፤ ውሉ በአዋዋይ ፊት የተደረገ ባይሆንም ውሉን ሳይክዱ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል በአዋዋይ ፊት አልተደረገም በሚል የሚቀርብ ክርክር ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ በመዝገብ ቁጥር 36887 የተሰጠው የሰበር ገዥ ውሳኔ የሚያመለክት መሆኑን፤ ውሉበተንኮልና በማታለል ስለመደረጉ የቀረበ ማስረጃ የለም በማለት ተጠሪዎች በሽያጭ ውሉ መሰረት ቤቱን እና ኦሪጅናል ሰነዶችን ለአመልካች ሊያስረክቡ ይገባል፤ እንዲሁም በሚመለከተው አካል ፊት ቀርበው በሽያጭ ውሉ መሠረት ስም ዝውውሩን ሊፈጽሙ ይገባል፤ አመልካችም የሽያጭ ቀሪ ክፍያ ለወራሾቹ በድርሻቸው ሊከፍሉ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

ከ3ኛ እስከ 6ኛ የተመለከቱት ተጠሪዎች ይህንን ውሳኔ በመቃወም ይግባኛቸውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የስር ፍ/ቤት ለውሳኔው መሰረት ያደረገው የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 36887 የሰጠው ውሳኔ ለጉዳዩ ተፈጻሚ

ለማድረግ ተጠሪዎቹ በመልሳቸው ውሉ በግልጽ መኖሩን በማመን ነገር ግን በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1723(1) ሥር የተመለከተውን መስፈርት አያሟላም የሚል መከራከሪያ ካነሱ ብቻ ስለመሆኑ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 149421 አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠበት በመሆኑ ከዚህ አንጻር ከ3ኛ እስከ 6ኛ የተመለከቱት ተጠሪዎች በስር ፍ/ቤት የሰጡት መልስ ሲታይ ውሉን በግልጽ ክደው የተከራከሩ መሆኑን የሚያሳይ እንጂ ውሉን አምነው በፎርማሊቲ ረገድ ብቻ የተከራከሩ መሆኑን የሚያመላክት ስላልሆነ በግራቀኙ መካከል የተደረገው የሽያጭ ስምምነት በህግ የተዘረጋውን ስርዓት ተከትሎ ያልተደረገ በረቂቅ ደረጃ ያለ በመሆኑ ግራቀኙ ከስምምነቱ በፊት ወደነበሩበት ሊመለሱ ይገባል በማለት የስር ፍ/ቤት ውሳኔን ሽሮ ግራቀኙ ወደ ነበሩበት የሚመለሱበት ሁኔታ ላይ እንዲወስን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 343(1) መሰረት መዝገቡን ወደ ስር ፍ/ቤት መልሶታል፡፡

ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም ይህንኑ የጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች መስከረም 30 ቀን 2016 ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተፈጽመዋል ያላቸዉን ስህተቶች በመዘርዘር እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡ የአቤቱታው ይዘትም በአጭሩ የጠቅላላ ቤትና ይዞታው 66.66% ባለቤቶች የሆኑት 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ውሉን ማድረጋቸውን አምነው መልስ በሰጡበት፣ የጠቅላላ ቤትና ይዞታው 24.99% ባለቤቶች የሆኑት ከ4ኛ እስከ 6ኛ የተመለከቱት ተጠሪዎችም ቤቱና ይዞታውን መሸጣቸውን አምነው በውሉ ፎርማለቲ ላይ ብቻ ክርክር ባነሱበት እንዲሁም የጠቅላላ ቤትና ይዞታ 8.33% ባለድርሻ የሆኑት 3ኛ ተጠሪ አመልካች በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 137 መሰረት 3ኛ ተጠሪ የፈረሙበት ውልን ለማያያዝ ባቀረብኩት አቤቱታ ላይ በሰጡት ምላሽ የሽያጭ ውሉን መፈረማቸውን አምነው እያለ የስር ጠቅላይ ፍ/ቤት ተጠሪዎች ውል ስለመኖሩ አላመኑም በማለት እና የውል ይፍረስልኝ የዳኝነት ጥያቄ ሳይቀርብለት ውሉ ፈርሶ ወደነበርንበት እንድንመለስ የሰጠው ውሳኔ ስህተት ነው፣ የስር ፍ/ቤት የይዞታው እና የቤቱ 91.66%ቱ ባለድርሻዎች ውሉን መኖሩን ሙሉ ለሙሉ በግልፅ ባመኑበት ውሉ በሁሉም ወገኖች እንደተካደ ቆጥሮ እና ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን የሰበር አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት በማድረግ ከጅምሩ ውል የለም ብሎ የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ተሽሮ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲፀናልኝ የሚል ነዉ፡፡

የሰበር አቤቱታዉ በሰበር ችሎት ተመርምሮ ከ3ኛ-6ኛ ተጠሪዎች ውሉ መደረጉን ክደው ተከራክረዋል ከሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሉ ሊፈርስ ይገባል በማለት የሰጠው ውሳኔ በተለይም ከ4ኛ-6ኛ ተጠሪዎች በጽሑፍ ያቀረቡትን መልስ ትክክለኛ ይዘት ያገናዘበ መሆን አለመሆኑን እንዲሁም እንደውሉ ቢፈጸም ተቃውሞ የሌላቸው 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ለውሉ ምክንያት ከሆነው ንብረት ያላቸው ድርሻ 66.66% መሆኑን ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለመሆኑን ግራ ቀኝ በተገኙበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል ተብሏል፡፡ በዚሁም መሠረት ተጠሪዎቹ በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ጥር 16 ቀን 2015 ዓ.ም አዘጋጅተው ባቀረቡት መልስ ተጠሪዎች ከአመልካች ጋር ያደረግነው ውል ሕጉን ተከትሎ ያልተደረገ ነው ተብሎ በስር ፍ/ቤት የተወሰነ በመሆኑ እና ብቻዬን ምንም ማድረግ አልችልም የሚል ይዘት ያለዉ መልስ አቅርበዋል፡፡ ከ3ኛ እስከ 6ኛ የተመለከቱት ተጠሪዎች ነሐሴ 2 ቀን 2016 ዓ/ም አዘጋጅተው ባቀረቡት መልስ ከድርሻ አንጻር ያስቀርባል በሚል የተያዘው ጭብጥ የማስረጃ ምዘና ጉዳይን ወይም የፍሬ ነገር ክርክር የሚመለከት በመሆኑ ሰበር ሰሚው ችሎት በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4) አንፃር ስልጣን የለዉም፡፡ በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በነበረ ክርክር ውል አለመኖሩን በግልጽ ክደን ተከራክረናል፣ የከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው

ፍርድ በፍ/ሕ/ቁ 1720 መሰረት በውል አዋዋይ ፊት ባልተደረገ የሽያጭ ውል ተጠሪዎች በሕግ ያገኙትን መብት የሚያሳጣ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት መሻሩ አግባብ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉን ዉሳኔ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ለጠየቁት ዳኝነት መሠረት ያደረጉት ከተጠሪዎች ጋር በተደረገዉ ዉል ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት የገዛ ቢሆንም ቀሪዉን ክፍያ ተቀብለዉ ቤቱን ከነይዞታዉ እንዲሁም ቤቱን የሚመለከቱ ሰነዶችን ለአመልካች ለማስረከብ ፈቃደኛ አለመሆናቸዉን ሲሆን፣ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ዉሉ መደረጉን አምነዉ የተከራከሩ ሲሆን ከ3ኛ-6ኛ ተጠሪዎች በበኩላቸዉ አመልካች ለክሱ መሠረት ያደረገዉ ዉል ሐሰተኛ እና በተንኮል የተደረገ ከመሆኑም በላይ 3ኛ ተጠሪም በዉሉ ላይ ያልፈረመ መሆኑን ጠቅሰዉ ክሱ ዉድቅ እንዲሆን የተከራከሩ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ ይህም በአጠቃላይ የሚያሳየዉ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ዉሉን አምነዉ መከራከራቸዉን፣ በአንፃሩ ከ4-6ኛ ተጠሪዎች ዉሉ ስለመደረጉ ጭምር ክደዉ መከራከራቸዉን ነዉ፡፡ እንግዲህ የተጠሪዎች ክርክር ይህ ከሆነ፣ ዉሉ ሙሉ በሙሉ ሊፈርስ ይገባል ወይስ ዉሉን ባመኑት 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ልክ ተፈፃሚ ሆኖ ሊቀጥል ይገባል? የሚለዉ ነጥብ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያሻዉ ነጥብ ነዉ፡፡

በመሠረቱ በመርህ ደረጃ፣ ሌሎች አስገዳጅ የህግ ድንጋጌዎችን መሠረት ባደረገ መልኩ፣ ተዋዋይ ወገኖች ዉላቸዉን በፈለጉት ዓይነት ፎርም እና ሁኔታ ቢዋዋሉ ዉላቸዉ የህግ ደረጃ ተሰጥቶት የሚያስገድዳቸዉ ሲሆን፣ የዉሉን ጉዳይ መሠረት በማድረግ ዉሉ የተወሰነ ፎርም ተከትሎ እንዲደረግ በህግ በልዩ ሁኔታ የተመለከተ እንደሆነ ተዋዋይ ወገኖች ዉላቸዉን በህግ በተወሰነዉ ፎርም መሠረት የማድረግ ግዴታ እንዳለባቸዉ እና ይህን ካላደረጉ ዉሉ ህጋዊ ዉጤት እንደማያስከትል በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1678፣ 1719 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡ ልዩ የአፃፃፍ ሥርዓትን ተከትለዉ እንዲደረጉ በህግ ከተለዩት የዉል ጉዳዮች ዉስጥ አንዱ የማይንቀሳቀስ ንብረትን አስመልክቶ የሚደረግ ዉል ሲሆን፣ በዚህም መሠረት የማይንቀሳቀስ ንብረትን አስመልክቶ ባለቤትነት ወይም የአላባ ወይም የመያዣ ወይም ሌላ አገልግሎት ለማቋቋም የሚደረጉ ዉሎች በጽሑፍ ሆነዉ ዉል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠዉ አካል ፊት መደረግ እንደለባቸዉ የህጉ አንቀጽ 1723(1) ድንጋጌ ያሳያል፡፡ ምንም እንኳ ይህ ድንጋጌ ዉሉ በጽሑፍ ሆኖ ነገር ግን በሚመለከተዉ አካል ዘንድ ቀርቦ ካልተረጋገጠ (ካልተመዘገበ) ዉጤቱ ምን እንደሆነ በግልጽ የማያስቀምጥ ቢሆንም፣ በህግ በልዩ ሁኔታ የተመለከተዉን ፎርም ተከትሎ ያልተደረገ ዉል ረቂቅ ሆኖ እንደሚቀር በህጉ አንቀጽ 1720(1) ላይ ከተመለከተዉ ድንጋጌ ጋር በጣምራ ሲነበብ ዉሉ ህጋዊ ዉጤት የማያስከትል መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 21448 ላይ የሰጠዉ አስገዳጅ የህግ ትርጉምም ይህንኑ የሚያሳይ ነዉ፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ ዉሉ መደረጉን ግራ ቀኝ የተማመኑ እንደሆነ ወይም ተዋዋዮች ካልተካካዱ ዉሉ ህጋዊ ዉጤት እንደሚያስከትል የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 36887 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ ከዚህ አኳያ ሲታይ ከ3-6ኛ ተጠሪዎች ዉሉ ስለመኖሩ ክደዉ የተከራከሩ ሲሆን፣ ዉሉም ስልጣን ባለዉ አካል

ዘንድ ቀርቦ ያልተመዘገበ ስለመሆኑ ግራ ቀኙን ያላከራከረ በመሆኑ ዉሉ በእነርሱ (ከ3-6ኛ ተጠሪዎች) ላይ ህጋዊ ዉጤት የሚያስከትል አይሆንም፡፡

በሌላም በኩል፣ ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ፣ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ዉል ስለማድረጋቸዉ ክደዉ አልተከራከሩም፡፡ ይልቁንም በዉሉ መሠረት ቤቱን ለአመልካች ለማስተላለፍ ፈቃደኛ መሆናቸዉን ጠቅሰዉ ለስር ፍርድ ቤት መልስ ያቀረቡ ስለመሆኑ ከስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ዉሉን ተገደዉ ሊፈጽሙ እንደሚገባ በስር የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠዉን ዉሳኔ በመቀበላቸዉም ከ3-6ኛ ተጠሪዎች ጋር በመሆን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አላቀረቡም፡፡ ምንም እንኳ፣ ከላይ እንደተገለጸዉ፣ ሽያጭን ጨምሮ የማይንቀሳቀስ ንብረትን አስመልክቶ የሚደረጉ ዉሎች ስልጣን ባለዉ አካል ዘንድ መመዝገብ እንዳለባቸዉ በሕጉ አንቀጽ 1723(1) ድንጋጌ በህጉ አንቀጽ 1720 ላይ ከተመለከተዉ ድንጋጌ አንፃር ሲታይ፣ በዚህ አግባብ ያልተደረገ ዉል ህጋዊ ዉጤት ሊያስከትል እንደማይችል የተመለከተ ቢሆንም፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 36887 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት ላይ ዉሉ ስልጣን ባለዉ አካል ዘንድ ቀርቦ ባለመደረጉ ምክንያት ዉሉ ህጋዊ ዉጤት እንዳይኖረዉ የሚደረገዉ ዉሉ ስለመደረጉ ተዋዋዮች ክደዉ ከተከራከሩ ብቻ ነዉ፡፡ ከዚህም የምንረዳዉ ዉሉ መደረጉን ተዋዋዮች ክደዉ እስካልተከራከሩ ድረስ ፍርድ ቤቶች ዉሉን የማስፈጸም ኃላፊነት ያለባቸዉ መሆኑን ነዉ፡፡ ከዚህ አኳያ ሲታይ ለክርክሩ መነሻ ከሆነዉ ቤትና ይዞታ ዉስጥ 66.66% ድርሻ ያላቸዉ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ዉሉ ስለመደረጉ ክደው ያልተከራከሩ ከመሆኑም በላይ በዉሉ መሠረት ለመፈጸም ፈቃደኛ መሆናቸዉን ጠቅሰዉ መልስ የሰጡ በመሆኑ በድርሻቸዉ ልክ ዉሉ የሚፈርስበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ በሌላ አነጋገር 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪ በየቅደም ተከተላቸዉ ከንብረቱ ባላቸዉ 50% እና 16.66%፣ በድምሩ 66.66% ልክ ሊጸና ይገባል፡፡

ከዚህ ሁሉ አንፃር ሲታይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ዉሉ ሊጸና አይገባም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ ዉሉን ክደዉ ከተከራከሩት ከ3-6ኛ ተጠሪዎች አኳያ ተገቢ ቢሆንም፣ ዉሉ ፈርሶ ግራ ቀኝ ከዉሉ በፊት ወደነበሩበት ሁኔታ ሊመለሱ ይገባል በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ዉሳኔ**

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 235796 ላይ ሐምሌ 26 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ በሰበር ሥ/ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1) መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. ዉሉ ፈርሶ ግራ ቀኝ ከዉሉ በፊት ወደነበሩበት ሁኔታ እንዲመለሱ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠ የዉሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
3. ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ዉል ከ3-6ኛ ያሉትን ተጠሪዎች የማያስገድድ ሲሆን፣ በአንፃሩ ዉሉ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎችን ያስገድዳል ተብሎ ተወስኗል፡፡
4. አመልካች በንብረቱ ላይ በየቅደምተከተላቸዉ 50% እና 16.66% ድርሻ ያላቸዉን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎችን ተክተዉ 66.66% ድርሻ በመያዝ ከ3-6ኛ ተጠሪዎች ጋር ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤትና ይዞታ ተጋሪ እንዲሆኑ ተወስኗል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ዉሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸምዓላማ አያገለግልም!

5. ዉሉ ከ3-6ኛ ተጠሪዎች ጋር በተያያዘ ፈራሽ በመሆኑ፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተዘግቶ የነበረዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ በዉሉ መሠረት አመልካች ለ3ኛ-6ኛ ተጠሪዎች የከፈሉት ክፍያ ካለ መጠኑን በማጣራት ተገቢዉን እንዲወስን መዝገቡ በሰበር ሥ/ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(2) መሠረት ተመልሶለታል፡፡
6. በመሆኑም በአመልካች እና ከ3-6ኛ ተጠሪዎች መካከል ለክርክሩ መነሻ በሆነዉ ቤትና ይዞታ ላይ የሚኖራቸዉን ግንኙነት አስመልክቶ ከጋራ ባለሀብትነት ጋር በተያያዘ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1257 እና ተከታዮቹ ላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደየአግባብነታቸዉ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡
7. ይህ ችሎት የካቲት 13 ቀን 2016 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ እግድ ተነስቷል፡፡
8. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ፋ/ዘ**

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ.መ.ቁ.253916

የካቲት 28 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች፡......1. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

2. እንዳሻዉ አዳነ

3. ቀነዓ ቂጣታ

4. ተሾመ ሽፈራዉ

5. ብርቅነሽ እሱባለዉ

አመልካች፡ ........ጠቋሬ ፈለቀ - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡...............አባ ምትኩ ዘዉዴ - የቀረበ የለም

ይህ መዝገብ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ይህ የአፈጻጸም ክርክር የተጀመረዉ በአማራ ክልል በዳህና ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች የሥር ፍርድ ባለመብት፣ የአሁን ተጠሪ የሥር የፍርድ ባለዕዳ ሆኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ አመልካች የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.0337693 ሰኔ 15 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ፡፡

**ማስታወሻ፡** - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ በግራ ቀኛዉ መካከል በነበረዉ የይዞታ ክርክር የሥር የወረዳዉ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ለክርክር መነሻ የሆነዉን ይዞታ ለቆ ለአመልካች እንዲያስረክብ መወሰኑን መዝገቡ ያሳያል። የአሁን አመልካች ፍርዱን ለማስፈጸም የአፈጻጸም አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን የወረዳዉ ፍ/ቤቱ የአሁን አመልካች በይዞታዉ ላይ ባለመብት ከመሆኑ በፊት የአሁን ተጠሪ በይዞታዉ ላይ ሁለት ክፍል ያለዉን ቤት መስራቱን በማረጋገጥ አመልካች የቤቱን ግምት ለተጠሪ እንዲከፍልና ተጠሪ ይዞታዉን ለቆ ለአመልካች እንዲያስረክብ ብይን መስጠቱን የዉሳኔዉ ግልባጭ ያመለክታል። በየደረጃዉ ያሉት የክልሉ ፍ/ቤቶችም የቀረበላቸዉን ቅሬታ ዉድቅ በማድረግ የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማጽናት መወሰናቸዉን የሥር ፍ/ቤት የዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል። የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ።

የአሁን አመልካች መስከረም 4 ቀን 2016 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ የአሁን ተጠሪ በዋናዉ ጉዳይ ላይ ተከራክሮ የቤት ግምት ካሳ እንዲከፈለዉ የፍርድ ባለመብት ባልሆነበት የሥር ፍ/ቤት በዋናዉ ፍርድ የቤት ግምት ካሳ ጉዳይ ለተጠሪ እንዲከፈል ባልተወሰነበት፣ ተጠሪ በይዞታዉ ላይ በሕገወጥ መንገድ ቤቱን ሲሰራ አመልካች እየተቃወምኩት መሆኑን ተረጋግጦ ባለበት የሥር ፍ/ቤት በዋናዉ ፍርድ መሰረት ለክርክር መነሻ የሆነዉን 10 በ15 ካ.ሜ የሆነዉን ይዞታ ተጠሪ ለአመልካች እንዲለቅ ማስፈጸም ሲገባዉ አመልካች ለተጠሪ የቤቱን ግምት እንዲከፍል መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲታረምልኝ በማለት በዝርዝር አመልክቷል።

ይህ ሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ባዘዘዉ መሰረት በ21/05/2017 ዓ.ም በተጻፈ መልስ፡ የሥር የወረዳዉ ፍ/ቤት የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰጠዉ ዉሳኔ መሰረት ለክርክር መነሻ በሆነዉ ይዞታ ላይ ያለዉን ቤት ባለሙያ በማስገመት አመልካችን ይህን ግምት ለተጠሪ እንዲከፍል መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት በመሆኑ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ዉድቅ ሆኖ የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ እንዲጸናልኝ በማለት በዝርዝር ተከራክሯል። የአሁን አመልካች የመልስ መልስ ባለመቅረቡ ታልፏል።

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር እና ለሰበር አቤቱታዉ መነሻ የሆነዉን የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል። እንደመረመርነዉ በዚህ ጉዳይ ምላሽ ማግኘት ያለበት ፣የክልሉ ሰበር ችሎት አመልካች አከራካሪዉ ይዞታ ላይ ያለዉን የሁለት ክፍል ቤት ግምት ለተጠሪ እንዲከፍል ተጠሪ ይዞታዉን ለአመልካች ለቆ እንዲያስረብክ በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ተገንዝበናል። በዚህ መሰረት በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በነበረዉ የአፈጻጸም ክርክር የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ጉዳዩን በመመርመር በሰጠዉ ዉሳኔ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት የአፈጻጸም ትዕዛዝ በመሻር የሥር የወረዳዉ ፍ/ቤት ዉሳኔ በሰጠበት ይዞታ ላይ ቤት መኖር አለመኖሩን በማጣራት በሕጉ አግባብ እንዲያስፈጽም መመለሱን መዝገቡ ያመለክታል። በዚህ መሰረት የሥር የወረዳዉ ፍ/ቤት ጉዳዩን በማጣራት ተጠሪ በይዞታዉ ላይ ሁለት ክፍል ያለዉን ቤት መስራቱን በማረጋገጥ የቤቱን ግምት በባለሙያ በማስገመት ተጠሪ ዉሳኔ ያረፈበትን ይዞታ ለአመልካች ለቆ እንዲያስረክብ፣ አመልካች ደግሞ በይዞታዉ ላይ ያለዉን ቤት

ግምት ለተጠሪ እንዲከፍል መወሰኑን የዉሳኔዉ ግልባጭ ያሳያል፡፡ በየደረጃዉ ያሉት ፍ/ቤቶችም ጉዳዩን በማየት አመልካች በይዞታዉ ላይ ያለዉን ቤት የባለሙያ ግምት ለተጠሪ እንዲከፍል መወሰኑን ማየት ይቻላል፡፡ በሥር ፍ/ቤት ከተረጋገጠዉ ፍሬ ነገር መረዳት እንደሚቻለዉ አመልካች በይዞታዉ ላይ ባለመብት ከመሆኑ በፊት ተጠሪ በይዞታዉ ላይ ቤቱን መስራቱን ያመለክታል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህንኑ ሁኔታ በመገንዘብ በይዞታዉ ላይ በተጠሪ የተሰራ ቤት ካለ ተጣርቶ አፈጻጸሙ በሕጉ አግባብ እንዲፈጸም በወሰነዉ መሰረት የሥር ፍ/ቤት ተጠሪ አከራካሪዉን ይዞታ ለአመልካች እንዲለቅ የተወሰነ በመሆኑ ይዞታዉን ለቆ ለአመልካች ማስረከቡ ግዴታ ቢሆንም አስቀድሞ የሰራዉን ቤት በተመለከተ በባለሙያ ተገምቶ የቀረበዉን ዋጋ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል መደረጉ፣ ለአመልካች በፍርዱ መሰረት እንዲፈጸምለት ያለዉን መብት እና የተጠሪ ንብረት የማፍራት መብት በማመዛዘን መወሰኑን ያስገነዝባል፡፡ ይህ ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.378 (1)፣ 392 ድንጋጌዎች የተመለከተዉን የፍርድ አፈጻጸም የሚመራበትን መርህን የሚቃረን ሆኖ አልተገኘም፡፡

እንደሚታወቀው የመጨረሻ ዉሳኔ ያገኘ የክልል ጉዳይ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ታይቶ ሊታረም የሚችለዉ በፌዴራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2 (4) እና 10 (1) (ሐ) (መ) ሥር ከተመለከቱት መስፈርቶች መካከል አንዱን የሚያሟላ ሆኖ ፍትህን የሚያዛባ ጉልህ የሕግ ስህተት ያለበት መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነዉ፡፡ ከዚህ ዉጭ ግን የመጨረሻ ዉሳኔ ያገኘ የክልል ጉዳይ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ የሚታይበት የሕግ አግባብ አይኖርም፡፡ ከዚህ አንጻር አሁን የተያዘዉ ጉዳይ ሲታይ የክልሉ ሰበር ችሎት የሥር ፍ/ቤቶች ፍሬ ነገርን አጣርተዉ ለመወሰን በሕግ በተሰጣቸዉ ስልጣን መሰረት ተጠሪ በይዞታዉ ላይ የሰራዉን ቤት በባለሙያ በማስገመት አመልካች የቤቱን ግምት ለተጠሪ እንዲከፍል፣ ተጠሪ ዉሳኔ ያረፈበትን ይዞታ ለአመልካች ለቆ እንዲያስረክብ የወሰኑት በማጽናት የሰጠዉ ዉሳኔ የሚነቀፍበት የህግ አግባብ የለዉም ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በዚህ ጉዳይ ያሳለፈዉ ዉሳኔ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ዉሳኔ

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.0337693 ሰኔ 15 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9 (1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. ግራ ቀኛቸዉ የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

## ትዕዛዝ

- የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
- ይህ ዉሳኔ በ3/7/2017 ዓ.ም ተነቧል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ አምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

**ማስታወሻ፡** - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

መ/ዐ

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
## የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 254020

የካቲት 26 ቀን 2017ዓ/ም

ዳኞች፡-ገበየሁ ፈለቀ

አለማየሁ ሹናራ

ደረጀ አያና

ኑረዲን ከድር

ብርሃኑ መንግስቱ

አመልካቾች፡- 1.አቶ አመድ ሙሜ

2.አቶ ኢብራሂም ሙሜ — አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አሚናት ኡስማን

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የገጠር መሬት ውርስን የሚመለከት ሲሆን ጉዳዩ በጀመረበት የሀረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን አመልካቾች ተከሳሽ፤ የአሁን ተጠሪ አውራሽ የሆኑት ወ/ሮ ከዲጃ ዑመር ከሳሽ ነበሩ፡፡ የአሁን ተጠሪ አውራሽ ያቀረቡት ክስም፡- ሟች አባታቸው በ1966 ዓ.ም በሞት የተለዩ መሆኑን፤ሟች አባታቸው እርሳቸውንና ሟች ወንድማቸውን አቶ ዘከሪያ ኡመር የወለዱ መሆኑን፤ሟች ወንድማቸውም የአሁን አመልካቾችን እናት አግብቶ ሲኖር ቆይቶ ልጅ ሳይወልድ እና ሳይናዝ የሞተ መሆኑን፤ ለክርክር መነሻ የሆነው በአራት ቦታ የሚገኘው የገጠር መሬት የሟች አባታቸው እና ክፍፍል ያልተፈጸመበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

እንዲሁም ከሟች ወንድማቸው ጋር ሲጠቀሙበት የቆዩ መሆኑን፤ ሟች ወንድማቸው ከሞተ በኋላም የአሁን አመልካቾች እናት እየረዳቻቸው በመሬቱ ስትጠቀም እንደነበር፤ እርሷ ከሞተች በኋላ መሬቱን ተጠሪዎች እንዲለቁ ቢጠየቁ ፈቃደኛ ሊሆኑ አለመቻላቸውን ጠቅሰው መሬቱን ለቀው እንዲያስረክቡኝ እና ከመሬቱ የተገኘውን ጥቅም ጨምረው እንዲከፍሉኝ የሚል ነበር፡፡ ተጠሪዎች ለክሱ ባቀረቡት መልስ ክሱ በይርጋ የተቋረጠ ነው፡፡ ለክርክር መነሻ የሆነውን መሬት እናታችን መብት በመመስረት ንብረትነቱ የመንግስት በሆነ መሬት ላይ ከከሳሽ ወንድም ጋር ባልና ሚስት በመሆን ጋብቻው በሞት ቀሪ እስከሆነበት ጊዜ ድረስ መብት ፈጥረው እየተጠቀሙ የቆዩ በመሆኑ ክሱ ውድቅ እንዲደረግልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

ፍ/ቤቱም በአሁን አመልካቾች የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውደቅ በማድረግ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ በሰጠው ውሳኔ የተጠሪ አውራሽ ለክርክር መነሻ የሆነውን መሬት በተዋረድ ከአባታቸውና ከወንድማቸው እንዳገኙት፤ ከአመልካቾች እናት ጋርም ይጠቀሙበት እንደነበር፤ ወራሽነታቸውንም ያረጋገጡ መሆኑን፤በሌላ በኩል አመልካቾች በእናታቸው ስም ለእርሻ ይዞታው ይከፈልበት የነበረ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ከማቅረብ ውጭ በይዞታው ላይ መብት ያላቸው መሆኑን በበቂ ሁኔታ አለማስረዳታቸውን፤ ይዞታው በእጃቸው ሊገባ የቻለው የከሳሽ ወንድም ሚስት በሆኑት እናታቸው አማካኝነት መሆኑ መረጋገጡን፤ መሬቱን በውርስም ሆነ በሌላ ህግ በእጃቸው እንዳልገባ ጠቅሶ መሬቱ ለከሳሽ /ለተጠሪ አውራሽ /ይገባል በማለት መሬቱን አመልካቾች እንዲያስረክቡ እና ለሶስት አመት የተገኘው ጥቅም ታስቦ ብር 202,950.00 እንዲከፍሉ ሲል ወስኗል፡፡

አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ይግባኝ ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ ሰበር ሰሚ ችሎቱ ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን በድጋሚ አይቶ እንዲወስን ከላከለት በኋላ የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት የአሁን ተጠሪ ተተኪ ወራሽ በመሆኗ መብት አላት በማለት የሥር ፍ/ቤቱን ውሳኔ አጽንቷል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁን 1ኛ አመልካች ቅር ተሰኝተው አቤቱታ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ችሎቱም ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ ካደረገ በኋላ በስር ፍ/ቤቶች የተፈጸመ የህግ ስህተት የለም ሲል የስር ፍ/ቤቶቹን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

የአሁን ሰበር ቅሬታ የቀረበውም በየደረጃው ያሉ ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት ለማስለወጥ ነው፡፡ የሰበር ቅሬታውም በአጭሩ፡- የተጠሪ አውራሽ ክስ ያቀረቡት ሟች አባታቸው ከሞቱ ከ38 አመት በኋላ እንዲሁም ሟች ወንድማቸው ከሞቱ ከ25 አመት በኋላ ሲሆን ወራሽ በሆኑና ወራሽ ባልሆኑ ሰዎች መካከል የሚቀርብ ክስም በ10 አመታት ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ የሚቋረጥ መሆኑ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በቅጽ 11 በመ/ቁጥር 59539 አስገዳጅ የሆነ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ይሁንና የስር ወረዳ ፍ/ቤት መቃወሚያውን ውደቅ ያደረገው ሲሆን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ደግሞ ይርጋውን በተመለከተ አግባብነት ያለው ህግ የፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1000/2/ ነው በሚል የይርጋ ክርክሩን ውደቅ በማድረግ የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ አጽንቷል፡፡ ስለሆነም የይርጋ ክርክሩ ውድቅ መደረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት

የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ አውራሽ ክስ በሚመሰርቱበት ወቅት ያላቀረቡትን የሟች ወንድማቸውን የወራሽነት ማስረጃ የአሁን ተጠሪ እንዲያቀርቡ መፈቀዱ የማስረጃ አቀራረብ ስርአትን ያልጠበቀና ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በቅጽ 15 በመ/ቁጥር 712980 ከሰጠው ውሳኔ ጋር የሚቃረን እና የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው፡፡ በሌላ በኩል ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 131533 ላይ ጭብጥ በመያዝ ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ጉዳዩን ሲመልስ ክሱን ከገጠር መሬት አዋጁ ጋር በማዛመድ እንዲመለከት የመለሰው ቢሆንም ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ከአዋጁ ጋር ሳይመለከት የወሰነ ሲሆን የተጠሪ አጎት ከወላጅ እናታችን ጋር ሲጋቡ የመሬት ባለቤትነቱ የመንግስት እና ህዝብ በሆነ ይዞታ ላይ የጋራ ባለይዞታነት መብት በመፍጠር ሀብት ንብረት ያፈሩበት ነው፡፡ በመሆኑም የተጠሪ አውራሽ ወንድሟን ለመውረስ አትችልም፡፡ የተቋረጠ ጥቅምን በተመለከተም ያቀረብነው አቤቱታ በዝምታ መታለፉ የህግ ስህተት ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው የሚሉ ናቸው፡፡

የአመልካቾች አቤቱታ ተመርምሮ የሥር ፍ/ቤቶች አከራካሪዎቹ አራቱም የገጠር ይዞታዎች ለተጠሪ ይገባል በማለት የወሰኑት ተጠሪ በሰ/መ/ቁጥር 131533 የሰበር ቅሬታ ማቅረባቸወን መሰረት በማድረግ የተሠጠ ውሳኔ ቢሆንም በዚህ ህዳር 28 ቀን 2010 በተሠጠው ውሳኔ አግባብ ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን የገጠር እርሻ መሬት አጠቃቀምና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 456/97 አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች እና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ህጎች መሰረት በማድረግ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሰረት ተጠሪ በተያዘው ጭብጥ ላይ የሰጡት መልስ በአጭሩ፡- የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰጠው ውሳኔ እና ትእዛዝ መሰረት ጉዳዩን ከአዋጅ ቁጥር 456/97 ጋር በማገናዘብ ያልመረመሩት ቢሆንም አመልካቾች በስር ወረዳ ፍ/ቤት በአዋጁ መሰረት እናታቸው በመሬቱ ላይ መብት ማግኘቷንና ቀጥሎም ይህ መብት ለእነርሱ የተላለፈ ስለመሆኑ ያቀረቡት ክርክር ባለመኖሩ አሁን በሰበር ደረጃ ሊያቀርቡ የሚችሉበት የህግ አግባብ ስለሌለ አቤቱታው ውደቅ ሊደረግ ይገባል፡፡ ይህ የሚታለፍ ቢሆን እንኳን የሟች ወ/ሮ ከዲጃ ዑመር ወንድም ከእህቱ ጋር በጋራ የሚወርሱትን ያልተከፋፈለ የውርስ ሀብት የሆነውን እና አራት ቦታ የሚገኙ የእርሻ መሬቶች እንደያዘ የአመልካቾችን እናት ማግባቱ በአዋጁ መሰረት ለሚስቱ ማውረስ ይችላል ቢባል እንኳን ሊያወርሳት የሚችለው የራሱን ግማሽ ድርሻ አጋማሽ ወይም 1/4ኛ ሊሆን ስለሚችል የተጠሪ ድርሻ 3/4ኛ በመሆኑ አመልካቾች የውርስ ሀብቱ በጠቅላላ ለእኛ ይገባል በማለት የሚያቀርቡት ክርክር የህግም ሆነ የሞራል ድጋፍ የሌለው ስለሆነ ውደቅ ሊደረግ ይገባል የሚል ነው፡፡ አመልካቾች የመልስ መልስ ያቀረቡ ሲሆን ክርክራቸውን አጠናክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለፀውን ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ፣ ከጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እና ቅሬታው ለሰበር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ነጥብ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተው መርምሮታል፡፡የመሬትና የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀምና

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

ጥበቃን በተመለከተ ለሚወጡ ህጎች በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 51(5) መሠረት የፈደራል መንግስት ሥልጣን ያለው ቢሆንም በአንቀጽ 52(2)(መ) ሥር እንደተደነገገው ክልሎች በፌዴራሉ መንግሥት የሚወጣውን የህግ መርህ በመከተል መሬትን ለማስተዳደር ህግ የማውጣት ሥልጣን የተሰጣቸው መሆኑን ያሳያል፡፡የገጠር መሬት ክርክር በተመለከተ ሊዳኙ የሚገባቸው በአዋጅ ቁጥር 456/97 እና በየክልሎቹ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ስለመሆኑ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 105092 ላይ በሰጠው ውሳኔ ትርጉም ሰጥቶበት ይገኛል፡፡ይህንን መሰረት በማድረግም የገጠር መሬት ክርክር በተመለከተ ሊዳኙ የሚገባቸው በአዋጅ ቁጥር 456/97 እና በየክልሎቹ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ስለመሆኑ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 105092 ላይ የሕግ ትርጉም የሰጠ ቢሆንም በሀረሪ ህዝብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ከገጠር መሬትና የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀምና ጥበቃ ጋር በተያያዘ የወጣ ህግ አለመኖሩ የኢፌዴሪ የገጠሪ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 456/97 ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያለው የህግ ማዕቀፍ መሆኑን ያሳያል፡፡

ለጉዳዩ አግባብነት ባለው የኢፌዴሪ የገጠሪ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 456/97 አንቀጽ 8(5) የቤተሰብ አባል የገጠር መሬት መውረስ እንደሚችሉ የተመለከተ ሲሆን በአንቀፅ 2(5) የቤተሰብ አባል ማለት የይዞታ ባለመብቱን መተዳደሪያ በመጋራት በቋሚነት አብሮ የሚኖርን ግለሰብ የሚወክል መሆኑ መመልከቱ ከመሬት ባለይዞታው ጋር በቋሚነት አብሮ የሚኖርና የራሱ ቋሚ መተዳደሪያ የሌለው ሰው የገጠር መሬት ሊወርስ የሚችል መሆኑን ያሳያል፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይ አከራካሪዎቹን የእርሻ ይዞታዎች ሟች ዘከሪያ ኡመር በመያዝ ለእርሻ ከቀድሞ ባለቤታቸው ጋር ሲጠቀሙባቸው ቆይተው ባለቤታቸው ስትሞትባቸው የአመልካቾችን እናት ያገቡ መሆኑን፤የአመልካቾች እናት አመልካቾችን ይዘው ወደ ሟች ዘከሪያ ኡመር ቤት ገብተው በእርሻው ከባለቤታቸውና ከአመልካቾች ጋር ሲጠቀሙ ቆይተው ሟች ዘከሪያ ከዚህ አለም በሞት ሲለዩ ለተጠሪ ድርሻቸውን እያካፈሉ አመልካቾችን በመያዝ ይዞታዎቹን በስማቸው አድርገው ሲጠቀሙ ቆይተው ከዚህ አለም በሞት የተለዩ መሆኑ ማስረጃን የመስማት፤የመመርመርና የመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡ይህም አመልካቾች የእርሻ ይዞታዎቹን በተመለከተ ከእናታቸው ጋር በመሆን በይዞታዎቹ ላይ ግማሽ የተጋሪነት መብት ያላቸው የቤተሰብ አባል መሆናቸውን በሚያሳይ መልኩ ከሟች ጋር ከመሬቱ የሚገኝ ገቢ በመጋራት አብረው ሲጠቀሙ የቆዩ መሆኑን እያሳየ ይህም አመልካቾች በእናታቸው ግማሽ ድርሻ ላይ በአዋጅ ቁጥር 456/1997 አንቀፅ 8(5) እና 2(5) መሰረት መብት ያላቸው መሆኑን እያሳየ የስር ፍርድ ቤቶች እነዚህን ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች ባላገናዘበ መልኩ የእርሻ ይዞታዎቹን በሙሉ ለቀው ለተጠሪ እዲያስረክቡና ለሶስት አመት የተገኘው ጥቅም ታስቦ ብር

202,950.00 እንዲከፍሉ መወሰናቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ውሳኔ

1. የሀረሪ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.08261 በ08/10/2007 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔና ይህንን ውሳኔ በማፅናት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.08297 በ02/09/2010 ዓ.ም በዋለው ችሎት እንዲሁም የሀረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.00253 ነሀሴ 23 ቀን 2015 ዓም የሰጠው ፍርድ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስነስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9(1)(ለ) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካቾች ለተጠሪ ሊያስረክቡ የሚገባው የአከራካሪዎቹን የእርሻ ይዞታዎች ግማሽ ድርሻ እንዲሁም ለሶስት አመት የተገኘውን ጥቅም በተመለከተም ለተጠሪ ሊከፍሉ የሚገባው ብር 101,475.00 (አንድ መቶ አንድ ሺህ አራት መቶ ሰባ አምስት ብር) ብቻ ሊሆን ይገባል በማለት ወስነናል፡፡

3.ግራ ቀኙ የሰበር ክርክሩን ወጪ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

**<u>መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡</u>**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

**<u>ማስታወሻ</u>፡** - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 256412

የካቲት 26 ቀን 2017ዓ/ም

ዳኞች፡-ገበየሁ ፈለቀ

ደረጀ አያና

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

ብርሃኑ መንግሥቱ

አመልካች፡- ቻይና ኮሙኒኬሽን ኩባንያ ግንባታ ወንጪ ደንዲ ኢኮቱሪዝም ፕሮጀክት - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ማንዴሳ ጪብሳ - ቀርቧል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ጉዳዩ የጉዳት ካሳ ክፍያን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በተጀመረበት በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ደግሞ በተከሳሽነት ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ፡- አመልካች ከደንዲ ሀይቅ እስከ ወንጪ ሀይቅ ያለው መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት ኮንትራክተር በመሆን በሚሰራበት ወቅት በደንዲ ወረዳ ገ/ጥራንት ሹቤሶሌ ተብሎ በሚጠራ አካባቢ ከሚገኘው ስፋቱ አራት ሂክታር በሆነው የእርሻ ይዞታዬ ላይ መንገድ ለመገንባት የቆፈረውን አፈር ጥቅምት 10 ቀን 2015 ዓ.ም በተሸከርካሪዎች ጭኖ በመድፋት በመሬቱን ገደላማ በማድረግ ከጥቅም ውጪ በመሆኑ በመሬቱ ላይ ተዘርቶ የነበሩትን የሰነፍ ቆሎ፤ገብስ እና ሚስር ቡቃያዎችን፤ለተለያየ አገልግሎት የሚውሉ በቁጥር 5,900.00(አምስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ባህር ዛፍ፤10 እግር ጥድ፤እንዲሁም 900 እግር ቀርከሃ ስላወደመብኝ

የእጽዋቶቹ እና የሰብል  ግምቱ ለወደፊት ያገኙ የነበረውን የ15 አመት ጥቅም በድምሩ ብር 9,823,000 (ዘጠኝ ሚሊየን ስምንት መቶ ሃያ ሶስት ሺ) የጉዳት ካሳ ከወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት ከሰዋል፡፡

አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ አፈር የተቆለለበት የመሬት ስፋት 0.375614 ሄክታር ብቻ መሆኑን፤ ከመሬቱ ላይ ሊገኝ የሚችለው የተቋረጠ ጥቅም እና የተለያዩ እጽዋት ግምት በደንዲ ወረዳ ካሣ ገማች ኮሚቴ ተሰርቶ የቀረበው የካሣ ግምት በድምሩ ብር 820,865.57(ስምንት መቶ ሃያ ሺህ ስምት መቶ ስልሳ አምስት ከ57/100) እንዲከፍል ቁጥሩ 51496 በሆነው መዝገብ ተወስኖ እያለ አዲስ ክስ መቅረቡ ተገቢ አለመሆኑን፤ አመልካች በ2015 ዓ.ም በተጠሪ ይዞታ ላይ አፈር አለመድፋቱን፤ደፍቷል ቢባል እንኳን አፈሩን በማንሳት መሬቱን ወደ ነበረበት መመለስ ስለሚቻል ቋሚ ጉዳት ባልደረሰበት እና የታጣ ጥቅም ሳይኖር የ15 ዓመት የተቋረጠ ጥቅም መጠየቁ የህግ ድጋፍ የሌለው መሆኑን፤ አመልካች ተጠያቂነት የለበትም እንጅ ተጠያቂ ነው ቢባል እንኳን በመሬቱ ላይ የደፋውን አፈር ማንሳት ወይም አፈሩን ለማስነሳት የሚያስፈልገውን ወጪ፤እንዲሁም በ2015 ዓ.ም ያልተሰበሰበ ሰብል እና በእፀዋቶቹ ላይ የደረሰውን ጉዳት ከመክፈል ባለፈ አመልካች ሌላ ኃላፊነት የሌለበት መሆኑን፤ አፈር የተጣለበት መሬት ላይ የሚገኙ እፀዋቾች ብዛት 1,262 እግር ብቻ መሆኑን፤የምርት እና እፀዋቱ ግምት ገምቶ ለማቅረብ በሕግ ሥልጣን ወይም ፈቃድ ባለው ድርጅት ወይንም አዋጁን ለማስፈጸም በመንግስት በተቋቋመ ኮሚቴ ስላልቀረበ በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 250 መሠረት ግምቱን እንደሚቃወሙ ጠቅሰው የቀረበው የካሣ ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ እና ተገቢ ነው ያለውን ማጣራት አድርጎ፡- አመልካች በተጠሪ ይዞታ ላይ አፈር በመድፋት የተለያዩ ሰብሎች እና እጽዋቶችን ማውደሙን የተጠሪ ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ቃል በአመልካች ምስክሮች አለመስተባበሉንና የማጣራት ሪፖርት ውጤቶችም የተጠሪ ምስክሮች የሰጡትን ምስክርነት የሚያጠናክር መሆኑን፤ክርክር ባስነሳው ይዞታ ላይ ያለአግባብ የተከመረው አፈር ለመንሸራተት የተጋለጠ በመሆኑ ማዕድንና ጥቅም ያለው አፈር ወደ ስር አልፎ ጠጠር እና ድንጋይ ያለው አፈር ደግሞ ከላይ በመሆኑና የመሬቱ አቀማመጥም አመቺ ስላልሆነ አፈሩን ከመሬቱ ላይ ማንሳት አስቸጋር እና የማይቻል መሆኑ በተደረጉ ማጣራቶች መረጋገጡን ጠቅሶ የማጣራት ሪፖርቱ የ15 ዓመት ካሣ መከፈል እንዳለበት መግለጹ መሬቱ ሙሉ በሙሉ ከጠቅም ውጪ መሆኑን ስለሚያመለክት አመልካች አፈሩን ማንሳት እየተቻለ ተጠሪ ካሳ መጠየቁ የህግ መሰረት የለውም ሲል ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት እንደሌለው ጠቅሶ ፤አፈር የተቆለለበት የይዞታ መጠን የእርሻ መሬት 0.4667 ሄክታር ሲሆን 0.3064 ሄክታር ደግሞ እፀዋት እንዳለበት በባለሙያ ተጣርቶ በቀረበው ሪፖርት ላይ ቅሬታ ባለመቅረቡ ጉዳት የደረሰበት የመሬት መጠን እንደሆነ ወስዶ ከዚህ መሬት ላይ የወደሙት ቋሚ እፀዋት ግምት ብር 751,000.00(ሰባት መቶ ሃምሳ አንድ ሺ.ህ)፤ የሰብሎቹን በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 1161/2011 አንቀጽ 13/1/ሐ/ እና በደንቡ አንቀጽ 26 መሠረት በእርሻ መሬቱ ላይ ላይ ቋሚ

ጉዳት በመድረሱ ተጠሪ በመሬቱ ላይ ጉዳት ከመድረሱ ከሶስት ዓመት በፊት ያገኝ ከነበረው ገቢ ውስጥ የአንድ ዓመቱን ከፍተኛ ዋጋ በመውሰድ በ15 አመት ተባዝቶ የሚመጣውን 72,371 x 15 =1,085,565.00 (አንድ ሚልዮን ሰማንያ አምስት ሺህ አምስት መቶ ስልሳ አምስት) እና በአትክልቶቹ ላይ የደረሰውን ጉዳት ብር 751,000.00(ሰባት መቶ ሃምሳ አንድ ሺህ) ጨምሮ በድምሩ ብር 1,836,565.00 (አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ ሰላሳ ስድስት ሺ አምስት መቶ ስልሳ አምስት ) ከወጪ እና ኪሳራ ጋር አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ባቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ጉዳዩን የተመለከተው ይግባኝ ሰሚው የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የይግባኝ አቤቱታው ያስቀርባል በማለት ግራ ቀኙን አከራክሮ በሰጠው ውሳኔ ስፋቱ 0.4667 ሄክታር በሆነው የተጠሪ የእርሻ መሬት ላይ አመልካች የደፋው አፈር በመሬቱ ላይ ተደልድሎ ለእርሻ የማያገለግል ከመሆኑም በላይ ከመሬቱ ላይ ሊነሳ እንደማይችል ስለተረጋገጠ ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 1161/2011 ቁጥር 8/1(ሰ) እና ቁጥር 12/1 መሠረት ካሣ የማግኘት መብት ስላለው በከፍተኛ ፍርድ ቤት የተወሰነው የካሳ መጠን እንዲከፈለው የተሰጠውን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

የሰበር ቅሬታ የቀረበውም በየደረጃው ያሉ ጉዳዩን የተመለከቱት የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት በሰበር ለማስለወጥ ሆኖ ይዘቱ፡- አመልካች ክርክር ካስነሳው መሬት አጠገብ ያለ ካሳ የተከፈለበት ሌላ መሬት ላይ የደፋው አፈር እንደ በድንገት ተንሸራቶ ክርክር ወደአስነሳው መሬት ከመደርመሱ ውጪ በተጠሪ መሬት ላይ አፈር አልደፋም፡፡ የኦሮሚያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት በተጠሪ መሬት ላይ የተደረመሰውን አፈር ማንሳት እንደሚቻል እና መሬቱ ምርት መስጠት እንደሚችል የሚገልጽ ሪፖርት ያቀረበ ሲሆን፤አፈሩ ከመሬት ያለው ከፍታ 15 ሳ.ሜ ብቻ ሆኖ በአከባቢ ካለው መሬት የተቆፈረ የአፈር የላይኛው ክፍል(Top Soil)ስለሆነ ባለበት በማስተካከል ምርት መስጠት እንደሚችል ሪፖርት ቀርቦ እያለ የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ በማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር መሰረት ያደረገ ስላልሆነ ተቀባይነት የለውም፡፡ ተጠሪ መጠየቅ የነበረበት ዳኝነት አፈሩ ከመሬቱ እንዲነሳ ወይም ለማንሳት የሚያስፈልገው ወጪ እና የ2015 ዓ.ም የተቋረጠ ገቢ እንዲከፈለው መሆን ሲገባው አፈሩ በመሬቱ ላይ በመደርመሱ ብቻ መሬቱ ላይ ቋሚ ጉዳት ደርሷል በሚል የ15 ዓመት የተቋረጠ ገቢ መጠየቁ አግባብ ካለመሆኑም በላይ አፈሩ መነሳት እንደሚችል እና መሬቱም ምርት መስጠት እንደሚችል ሪፖርት ቀርቦ እያለ አፈር በመሬቱ ላይ በመደፋቱ ብቻ ስፋቱ 0.4667 ሄክታር በሆነው የተጠሪ መሬት ላይ ዘላቂ ጉዳት ደርሷል በሚል 1,085,565.00 (አንድ ሚልዮን ሰማንያ አምስት ሺህ አምስት መቶ ስልሳ አምስት) ብር ካሣ እንዲከፈለው መወሰኑ የፍትሐ ብሔር ሕጉን ቁጥር 2090 እና 2091 ድንጋጌዎች የሚቃረን መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው፡፡ በሌላ በኩል ከምዕራብ ሸዋ ዞን የመሬት አስተዳደር እና ግብርና ጽ/ቤት የቀረቡ ሪፖርቶችን ፍርድ ቤቱ ውድቅ አድርጎ በገለልተኛ አካል ተጣርቶ ይቅረብ የሚል ትዕዛዝ ሰጥቶ በትዕዛዙ መሰረትም

ከኦሮሚያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የባለሙያ አስተያየት ከቀረበ በኋላ ይህን የባለሙያ ሪፖርት ወደ ጎን በመተው ወደ ኋላ ተመልሶ ውድቅ የተደረጉ ሪፖርቶችን መሠረት በማድረግ የሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል፡፡ የኦሮሚያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ባቀረበው ሪፖርት ክርክር ካስነሳው የእርሻ መሬት ውስጥ ስፋቱ 0.3064 በሆነው ሄክታር ላይ በግብርና ሳይንስ የችግኝ ተከላ እስታንዳርድ መሠረት 1,362 ዛፎች ብቻ መትከል እንደሚቻል፤ መከፈል ያለበት የ15 ዓመት የተቋረጠ ገቢም 551,610.00 (አምስት መቶ ሃምሳ አንድ ሺህ ስድስት መቶ አሥር) ብር ብቻ እንደሆነ የቀረበውን የባለሙያ አስተያየት በስር ፍርድ ቤቶች ውድቅ ተደርጎ ከምዕራብ ሸዋ ዞን የመሬት አስተዳደር እና ግብርና ጽ/ቤት የቀረበውን ቃለ ጉባኤ መሠረት በማድረግ የተሰጠው ውሳኔ ስህተት በመሆኑ አመልካች ብር 551,610.00 (አምስት መቶ ሃምሳ አንድ ሺህ ስድስት መቶ አሥር) ለተጠሪ እንዲከፍል እንዲወሰን ጠይቋል፡፡

በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 6/1 መሠረት ለሰበር ሰሚው ችሎቱ የተመራው የሰበር አቤቱታ በሰበር ሰሚ ችሎቱ ተመርምሮ አመልካች በአከራካሪው 0.4667 ሄክታር መሬት ላይ ጉዳት ስላልደረሰ ካሳ እንዲከፍል መወሰኑ አላግባብ ነው፤ ኃላፊነት አለበት የሚባል ከሆነም በ2015 ዓ.ም የተቋረጠ ገቢ እና አፈሩ ከመሬቱ ላይ እንዲነሳ ወይም ለዚህ የሚያስፈልገው ወጪ እንዲከፈል ብቻ ሊወሰን ይገባል በሚል ያቀረበውን ቅሬታ ተጠሪ ባሉበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ በሰጡት መልስ፡- ክርክር ባስነሳው መሬት ላይ ጉዳት ደርሷል አልደረሰም የሚለው ጉዳይ የማስረጃ ምዘና ስለምመለከት የሰበር ሰሚ ችሎቱ በዚህ አግባብ የቀረበውን አቤቱታ የማየት ሥልጣን የለውም፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች በተጠሪ መሬት ላይ ጉዳት መድረሱን፤ የደረሰው ጉዳትም ቋሚ መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ አመልካችም በስር ፍርድ ቤት መሬቱ ላይ ጉዳት መድረሱን አምኖ ተጠሪ ጉዳት በደረሰበት መሬት ላይ በ2014 ዓ.ም ካሳ በልቶበታል በሚል ስለተከራከረ ካሳ ያልተከፈለው መሆኑ ተረጋግጦ ውሳኔ ተሰጥቶ እያለ አመልካች በመሬቱ ላይ ጉዳት ያልደረሰ አስመስሎ የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ መሬቱ ተመልሶ ምርት መስጠት የማይችል ቋሚ ጉዳት የደረሰበት መሆኑ በባለሙያ ስለተረጋገጠ ተጠሪ መጠየቅ ያለበት የ2015 ዓ.ም የተቋረጠ ገቢ እና አፈሩ የሚነሳበትን ወጪ ብቻ ነው የሚለው የአመልካች አቤቱታ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ ጉዳቱ ቋሚ በመሆኑ መድረሱ የተረጋገጠው የጉዳት መጠን የ15 ዓመት ካሳ መከፈል እንዳለበት ከኦሮሚያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ባለሞያ የቀረበውን አስተያየት መሠረት አድርጎ የካሳ መጠኑ በ15 ዓመት ተባዝቶ መወሰኑ አግባብ ስለሆነ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ፀንቶ የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ እንዲነሳላቸው ጠይቀዋል፡፡

አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለ መልኩ የተመለከተው የግራ ቀኝ ክርክር እና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ውሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንፃር

የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ለማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ የግል ንብረት ባለቤት የመሆን መብት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40(1) ተከብሯል፡፡ ኢትዮጵያዊ ዜጋ በጉልበቱ ወይንም በገንዘቡ በመሬት ላይ ለሚገነባው ቋሚ ንብረት ወይንም ለሚያደርገው ቋሚ መሻሻል ሙሉ መብት ያለው መሆኑን፤ ይህ መብትም የመሸጥ ፤ የመለወጥ ፤ የማውረስ ፤ የመሬት ተጠቃሚነቱ ስቋረጥ ንብረቱን የማንሳት ፤ ባለቤትነቱን የማዛወር ወይንም የካሳ ክፍያ የመጠየቅ መብትንም እንደሚያካትት እና አፈፃፀሙ በሕግ እንደሚወሰን አንቀጽ 40(7) ያመለክታል፡፡ በንዑስ አንቀጽ 8 ድንጋጌ መሠረት የግል ንብረት መብት እንደተጠበቀ ሆኖ መንግስት ለሕዝብ ጥቅም ተመጣጣኝ ካሳ በቅድሚያ በመክፈል የግል ንብረትን ሊወስድ ይችላል፡፡ የመሬት ይዞታ እንዲለቅ ለተደረገ ባለይዞታ ተገቢና ተመጣጣኝ ካሣ እና የተነሽ ድጋፍ ለመክፈል ግምት ውስጥ መግባት የሚገባቸውን መሠረታዊ መርሆዎችን ለይቶ ለመወሰን፤ለህዝብ ጥቅም ሲባል የሚለቀቅ ንብረትን በሚመለከት ተመጣጣኝ ካሣ በቅድሚያ እንዲከፈል በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 40/8 እንዲሁም ተነሺዎች በመንግስት እርዳታ እንዲቋቋሙ በአንቀጽ 44(2) የተቀመጠውን መሠረት ሀሳብ በዝርዝር መደንገግ አስፈላጊ በመሆኑ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበት፤ካሣ የሚከፈልበት እና ተነሽዎች መልሶ የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ለመሰወን አዋጅ ቁጥር 1161/2011 መወጣቱን የአዋጁ መቅደም(preamble) ያመለክታል፡፡ የዚህ አዋጅ ተፈፃሚነት ወሰንም ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበት፤ካሣ የሚከፈልበት እና ተነሽዎች መልሶ የሚቋቋሙበትን ሁኔታ በሚመለከት በሀገሪቱ በከተማም ሆነ በገጠር ተፈፃሚነት እንዳለው የአዋጁ አንቀጽ 3 ድንጋጌ ያመለክታል፡፡ በቁጥር 11 ድንጋጌ መሠረት ለህዝብ ጠቅም መሬት እንዲለቀቅ ሲደረግ ተነሽው ባለው የንብረትና ይዞታ መብት መሠረት የንብረት እና ልማት ተነሽ ካሣ ይከፈለዋል፡፡ የሚከፈለው ካሣም በመሬቱ ላይ ለሚገኘው ንብረት እና በመሬቱ ላይ ለተደረገው ቋሚ መሻሻል እንደሆነ ከአዋጁ ቁጥር 12 ድንጋጌ መረዳት ይቻላል፡፡ በልማት ምክንያት በቋሚነት ይዞታውን እንዲለቅ የሚደረግ የገጠር መሬት ባለይዞታ ከተወሰደበት መሬት ተመጣጣኝ ምርት የሚያስገኝ ምትክ መሬት የሚሰጠው መሆኑንና ተመጣጣኝ ምትክ መሬት የማይሰጥ ከሆነ መሬቱን እንዲለቅ ከመደረጉ በፊት በነበሩት ሶስት ዓመታት ውስጥ ከመሬቱ ሲያኝ የነበረውን ከፍተኛ ዓመታዊ ገቢ በአስራ አምስት ተባዝቶ የልማት ተነሽ ካሣ እንደሚከፈል ከአዋጅ  አንቀጽ 13/2 (ሀ) እና (ሐ) ድንጋጌ መረዳት ይቻላል፡፡ በቋሚነት ከመሬቱ ለሚፈናቀሉት የመፈናቀያ ካሣ የሚከፈለው በደንብ ቁጥር 135/1998 መሠረት ተሰልቶ ነው፡፡ በጊዜያዊነት ለሚነሳ የገጠር መሬት ባለይዞታ የሚሰጥ የልማት ተነሽ ካሣ መጠን የመሬቱን ምርታማነት ወደ ነበረበት ለመመለስ የሚወስደው በአከባቢው የግብርና ተቋም የሚወሰን ተጨማሪ ጊዜ ታሳቢ ማድረግ ያለበት መሆኑን፤መሬቱ በፊት ይሰጥ የነበረውን አገልግሎት መስጠት የማይችል ከሆነ በቋሚነት እንደለቀቀ ተቆጥሮ በአንቀጽ 13/1 መሠረት የልማት ተነሺ ከሳ ወይም

ምትክ ቦታ ይሰጠዋል፡፡(የአዋጅ ቁጥር 1161/2011 አንቀጽ 13/2(ለ) እና (ሐ) ድንጋጌዎችን ይመለከቷል፡፡

በንብረቱ ህጉ እና በህገ መንግስት የተጠበቀው የአንድ ሰው የንብረት መብት በሌላ ሰው ጥፋት በሆነ አድራጎት የተጎዳ መሆኑ ከተረጋገጠ ባለንብረት ከጥፋት ፈጻሚው ከደረሰበት የንብረት መብት ጉዳት ጋር እኩል፣ ተመጣጣኝነት ያለውን የካሳ መጠን የማግኘት መብት ያለው መሆኑን ከፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 2028፣ 2035፣ 2054፣ 2084/2፣ 2090፣ 2091፣ 2092 እና የንብረት ህግ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ ከውል ውጭ የመብት ጥያቄ (Tort claims) ካሳ የሚከፈለው ጉዳት መኖሩ ሲረጋገጥ ሲሆን የካሳ አተማመን፣ መጠንና አከፋፈልን በተመለከተ በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 2090፣ 2091፣ 2092፣ 2095 እና በሌሎች ድንጋጌዎች የተቀመጠ ጉዳይ ነው፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለውም ካሳው በተቻለ መጠን ለጉዳቱ ጋር መመጣጠን ያለበት መሆኑን ነው፡፡ ከውል ውጪ ኃላፊነትን ከሚመለከተው የፍትሐ ብሔር ሕጉ ድንጋጌዎች መረዳት እንደሚቻለው ለጉዳቱ መድረስ ምክንያት በሆነው ተግባርና በውጤት መካከል ግኑኝነት ያለ መሆኑን ሊረጋገጥ እንደሚገባ፣የሚከፈለው የካሣ ልክም ከደረሰው ጉዳት ተመጣጣኝ መሆን እንዳለበት ያስገነዝቡናል፡፡ በዚህም መሠረት ጉዳቱ በሰው መብት/ጥቅም ላይ በተጨባጭ ችግር ያደረሰ ወይም ወደፊት ችግር የሚያደርስ መሆኑን፣ የመብት/ጥቅም ጥሰቱ ማቴሪያሊዊ /በሰው አካል ወይም ንብረት የደረሠ/ ወይም ሞራላዊ ሊሆን እንደሚችል ከሕጎ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የጉዳት ካሣ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ ሲመዘንም በተጎጂው ላይ በእርግጠኝነት መድረሱ የታወቀ /actual damage/ ወይም ወደፊት ሊደርስ የሚችል ጉዳትን/future damage/ ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት የግድ የሚል መሆኑን ከፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 2091/1/ እና 2092 ድንጋጌዎች ይዘት ያስረዳሉ፡፡ ድንጋጌዎቹ የጉዳት ካሣ ሊተመን የሚገባ መሆኑን በግልጽ ከማስቀመጣቸው በተጨማሪ የአተማመኑ ሥርዓትም እንደጉዳቱ ዓይነትና ማስረጃ አቀራረብ ውስብስብነት ሊለያይ የሚችል መሆኑን ከፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር ቁጥር 2141 ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ በዚህም መሠረት የጉዳት ካሣ መጠን አጥጋቢና በቂ ማስረጃን ወይም ርትዕን መሠረት በማድረግ ሊወሰን ይችላል፡፡ ይህንኑ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በካሳው ላይ ዳኝነት ለመስጠት በቅድሚያ ሊወሰን የሚገባው ለጉዳቱ ኃላፊነት የሚወስደው ወገን መኖሩን በሚገባ ማረጋገጥ መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2027፣ 2028 እና 2029 ድንጋጌዎች ያስረዳሉ፡፡

በተያዘው ጉዳይ የተጠሪ ክርክር አመልካች በይዞታው ላይ አፈር በመድፋቱ በሰብል እና ቋሚ አትክልቶች ላይ ለደረሰው ጉዳት ተመጣጣኝ ካሣ ሊከፈለኝ ይገባል የሚል ስለሆነ ክርክሩ በመሠረታዊነት ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ ማስለቀቅ እና የንብረት ካሳ መክፈል (Expropriation) የሚመለከት ጉዳይ ሳይሆን ከውል ውጭ የመብት ጥያቄ (Tort claims) የሚከፈል

የጉዳት ካሳን የሚመለከት በመሆኑ በዋናነት መታየት የሚገባው የፍትሐ ብሔር ሕጉን ድንጋጌ መሠረት አድርጎ ነው፡፡ ይህ ማለት ግን ለደረሰውን ጉዳት ተመጣጣኝ የሆነ ካሳ እንዲከፈል ለማድረግ የፍትሐ ብሔር ሕጉን ክፍተቶች ለመሙላት ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበት፤ካሣ የሚከፈልበት እና ተነሽዎች መልሶ የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ለመሰወን የወጣው አዋጅ ቁጥር 1161/2011 ጥቅም ላይ እንዳይውል የሚከለክል አይደለም፡፡ ተጠሪ አመልካች በእርሻ ይዞታው ላይ መንገድ ለመገንባት የቆፈረውን አፈር ጥቅምት 10 ቀን 2015 ዓ.ም በተሽከርካሪዎች ጭኖ በመድፋት መሬቱን ገደላማ በማድረግ ከጥቅም ውጪ በመሆኑ በመሬቱ ላይ ተዘርቶ የነበሩትን የሰነፍ ቆሎ፤ገብስ እና ሚስር ቡቃያዎችን እና ብዛታቸው በክሱ ውስጥ የተመለከቱትን ቋሚ ተክሎችን እንዳወደመበት ገልጾ የወደሙ እጽዋቶች እና ሰብል ግምት የ15 አመት በድምሩ ብር 9,823,000 (ዘጠኝ ሚሊየን ስምንት መቶ ሃያ ሶስት ሺ) የጉዳት ካሳ ከወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፍለው ላቀረበው ክስ አመልካች በሰጠው መልስ አመልካች በ2015 ዓ.ም በተጠሪ ይዞታ ላይ አፈር አለመድፋቱን፤ደፍቷል ቢባል እንኳን አፈሩን በማንሳት መሬቱን ወደ ነበረበት መመለስ ስለሚቻል ቋሚ ጉዳት ባልደረሰበት እና የታጣ ጥቅም ሳይኖር የ15 ዓመት የተቋረጠ ጥቅም መጠየቁ የህግ ድጋፍ የሌለው በመሆኑ አመልካች ተጠያቂ መሆን ያለበት በመሬቱ ላይ የደፋውን አፈር ማንሳት ወይም አፈሩን ለማስነሳት የሚያስፈልገውን ወጪ እንዲሁም በ2015 ዓ.ም ያልተሰበሰበ ሰብል እና በእፀዋቶቹ ላይ የደረሰውን ጉዳት ብቻ መሆኑን ተከራክሯል፡፡

አመልካች በተጠሪ መሬት ይዞታ ላይ አፈር መድፋቱ እና አፈሩን ማንሳት እንደማይቻል በፍሬ ነገር ደረጃ ስለተረጋጠ አመልካች አፈር የደፋበት መሬት ላይ ለወደሙት ቋሚ ተክሎች ብር 751,000.00(ሰባት መቶ ሃምሳ አንድ ሺ.ህ) ብር እንዲከፍል መወሰኑ ተገቢ ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ ሰብሎችን በተመለከተ ጉዳቱ ከመድረሱ በፊት ባሉት ሶስት ዓመታት ሊገኝ ይችላል የተባለውን የተጣራ ገቢ ብር 72,371.00(ሰባ ሁለት ሺ.ህ ሶስት መቶ ሰባ አንድ) በአስራ አምስት ተባዝቶ ብር 1,085,565(አንድ ሚልዮን ሰማንያ አመስት ሺ.ህ አምስት መቶ ስልሳ አምስት) እንዲከፈል ሲወስን ለስሌቱ መሠረት ያደረገው አዋጅ ቁጥር 1160/2011 አንቀጽ 13(1) (ሐ) እና አዋጁን ለማስፈፀም የወጣውን ደንብ ነው፡፡ በድንጋጌ መሠረት በዚህ ስሌት ካሳ የሚከፈለው በቋሚ የልማት ተነሽነት ይዞታው ተወስዶበት ምትክ መሬት ላልተሰጠው ሰው ነው፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣን የተመለከተው የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እዚህ መደምደሚያ ላይ እንዲደርስ ያደረገው በተጠሪ መሬት ላይ የተደፋውን አፈር ማንሳት አስቸጋሪ እና የማይቻል መሆኑ በተደረጉት ማጣራቶች የተረጋገጠ በመሆኑና መሬቱ አስቀድሞ ወደነበረበት መመለስ የሚችል ቢሆንም የአስራ አምስት ዓመት ካሳ ብከፈል ይሻላል የሚል ሪፖርት ከኦሮሚያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ቀርቧል በሚል ነው፡፡ መሬቱ ከተጠሪ እጅ ባይወጣም የደረሰው ጉዳት ቋሚ ከሆነ ወይም በፊት ወደ ነበረበት ምርታማነት መመለስ ካልተቻለ ከመሬቱ የመፈናቀል ዓይነት ውጤት ስለሚኖረው በአዋጅ ቁጥር 1160/2011

አንቀጽ 13/2(ለ) እና (ሐ) ድንጋጌዎችን መሠረት መሬቱን በቋሚነት እንደለቀቀ ተቆጥሮ በአንቀጽ 13/1 መሠረት ካሳ ሊከፈል ይገባል፡፡ የመሬቱን ምርታማነት ወደ ነበረበት መመለስ እየተቻለ መሬቱን በቋሚነት እንደለቀቀ ተወስዶ ካሳ እንዲከፈል በአማራጭ በሕጉ ያልተመለከተ ከመሆኑም በተጨማሪ ተጠሪ በቋሚነት መሬቱን እንደለቀቁ ተወስዶ የአስራ አምስት ዓመት ካሳ እንዲከፈላቸው እንደአማራጭ የተወሰደበት ልዩ፤ ግልጽ እና አሳማኝ ምክንያት መኖሩን ውሳኔው ስለማያመለክት ለተጠሪ ሊከፈራቸው የሚገባው ካሳ ተመጣጣኝ መሆኑ ሳይጣራ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

**ውሳኔ**

1. የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት ታህሳስ 3 ቀን 2016 ዓ.ም በዋለው ችሎት መዝገብ ቁጥር 414303 ላይ የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 52535 ጥቅምት 14 ቀን 2016 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት የሰጠው ውሳኔ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ - ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 9(1/ለ) መሠረት **ተሻሽሏል፡፡**

2. አመልካች በተጠሪ ቋም አትክልቶች ላይ ላደረሰው ጉዳት 751,000.00(ሰባት መቶ ሃምሳ አንድ ሺ.ህ) ብር እንዲከፍል የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ፀንቷል(አልተነካም)፡፡

3. የብር 751,000.00(ሰባት መቶ ሃምሳ አንድ ሺ.ህ) 10% ማለትም 75,100(ሰባ አምስት ሺ.ህ አንድ መቶ) የጠበቃ አባል እንዲሁም 751,000.00(ሰባት መቶ ሃምሳ አንድ ሺ.ህ) ብር በታርፉ መሠረት የተከፈለውን ዳኘነት አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍሉ ተወስኗል፡፡

4. የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውሳኔ የዘጋውን የመዝገብ ቁጥር 52535 በማንቀሳቀስ ስፋቱ 0.4667 ሄክታር በሆነው የተጠሪ እርሻ መሬት ላይ የደረሰው ጉዳት ቋሚ ወይስ ጊዜያዊ? መሬቱ ወደነበረበት ምርታማነት ተመልሶ የቀደመ አገልግሎቱን መስጠት የሚችል መሆን አለመሆኑን፤መከፈል ያለበት ካሳ ምርታማነቱን ወደነበረት ለመመስ የሚወስደውን ጊዜ ታሳቢ ያደረገ መሆን አለበት ወይስ በቋሚነት መሬቱ የቀደመ አገልግሎት እንደማይሰጥ ተወስዶ ነው መሰላት ያለበት የሚለውን ጭብጥ አጣርቶ ተገቢ የሆነውን ህጋዊ ውሳኔ እንዲሰጥ መዝገቡ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 9/2 መሠረት መልሰንለታል፡፡

5. ለሰበር ክርክሩ የዋለውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የግላቸውን ይቻሉ፡፡

6. የውሳኔው ትክክለኛ ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይድረስ፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

መዝገቡ ውሳኔ አግኝቶ ስለተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

መ/ዐ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መዝገብ ቁጥር - 256463

ቀን - 28/06/2017 ዓ.ም

ዳኞች - ገበየሁ ፈለቀ

ዓለማየሁ ሹናራ

ደረጀ አያና

ኑረዲን ከድር

ብርሃኑ መንግስቱ

አመልካቾች -

1. አቶ ዮሐንስ ገ/ሚካኤል
2. አቶ ገብርኤል ገ/ሚካኤል
3. አቶ ማርቆስ ገ/ሚካኤል
4. አቶ ግዛቸው ገ/ሚካኤል
5. ወ/ሮ እየሩሳሌም ገ/ሚካኤል የቀረበ የለም

ተጠሪዎች -

1. ወ/ሮ ሃና ደርሶልኝ
2. አቶ ዳኛው ገ/ሚካኤል የቀረበ የለም

መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው ለምርመራ ስለሆነ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍርድ</u>

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች በቀን 15/04/2016 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 312575 በቀን

20/03/2016 ዓ.ም የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ብይን በማፅናት የሰጠው ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የመፋለም ክርክርን የሚመለከት ሆኖ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን በስር ፍርድ ቤት አመልካቾች የመቃወም አመልካቾች ተጠሪዎች የመቃወም ተጠሪዎች ሆነው ተከራክረዋል፡፡

አመልካቾች ሚያዚያ 2 ቀን 2015 ዓ.ም በተፃፈ የመቃወም አቤቱታ ሟች አባታቸው አቶ ገ/ሚካኤል ኃ/ማርያም በህይወት እያሉ እንዲሁም አባታቸው ከሞቱ በኃላ በስር ፍርድ ቤት ተጠሪ የሆኑት፣ አመልካቾችና የ 96 አመት የሆኑት የግራ ቀኙ እናት ጋር በአልኮልና በለስላሳ ማከፋፈያ እንዲሁም በሸቀጣሸቀጦች ጅምላ ንግድ ስራ ተሰማርተው በቁጥር ስምንት የሆኑ የተለያዩ ተሸከርካሪዎች፤ ደምቢዶሎ ከተማ ውስጥ የሚገኝ ሆቴል፣ የቡና ማበጠሪያ፣ የመጠጥ ማከፋፈያ፣ የመኖሪያ ቤትና መጋዘን፤ በቡና ግብይት ላይ የነበረ አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሺህ ብር፣ በአዋሽ ባንክ ያለ 50 የአክስዮን ድርሻ በጋራ ያፈሩ መሆኑንና ተጠሪዎች ጋብቻ ሲፈፅሙ እነዚህ ንብረቶች የአመልካቾች መሆናቸውን በጋብቻ ውላቸው ተስማምተዋል፡፡ እነዚህ ንብረቶች ከፊሎቹ ባሉበት ከፊሎቹ በሽያጭ ሆነ በሌላ መንገድ እየተለዋወጡና እየተቀላቀሉ ብዛታቸው 16 የሆኑ በተጠሪ ስም የተመዘገቡ የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች፤ በተጠሪ ስም የተመዘገቡ በአዋሽ ባንክ፣ በኦሮሚያ ባንክ፣ በህብረት ባንክ ያሉ አክስዮኖች፤ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ በአዋሽ ባንክ፣ በህብረት ባንክ፣ በኦሮሚያ ህብረት ስራ ባንክ፣ በኦሮሚያ ባንክ ተጠራቅሞ የሚገኝ ገንዘብ እና ተሸከርካሪዎች በቤተሰብ የተፈሩና በተጠሪዎች የጋብቻ ውል ላይም የቤተሰብ ንብረቶች መሆናቸው ተረጋግጦ እያለ ተጠሪዎች ከዚህ በተቃራኒ በሰበታ ከተማ የሚገኘውን በ 612 ካሬ ሜትር ላይ ያረፈ ቤት፣ በቄለም ወለጋ ዞን ደምቢዶሎ የሚገኘውን መኖሪያ ቤት እንዲሁም በዚህ ከተማ በ 2,000 ካሬ ሜትር ላይ ያረፈ ሆቴል ን በመተው ሌሎችን ንብረቶች የተጠሪዎች የጋራ ንብረት ነው በማለት ያስወሰኑ በመሆኑ ውሳኔው ቀሪ እንዲሆን በማለት የመቃወም አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡

1ኛ ተጠሪ ግንቦት 18 ቀን 2015 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ባቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የ 2ኛ ተጠሪና የአመልካቾች አባት የሆኑት ሟች ገ/ሚካኤል ከዚህ አለም በ 1972 ዓ.ም የተለዩና አቤቱታው በ 2015 ዓ.ም ከ 43 አመታት በኃላ የቀረበ በመሆኑ በፍ/ብ/ህ አንቀፅ 1000(1) እና (2) መሰረት በ 3 አመት ይህ ከታለፈ በ 15 አመታት ይርጋ ይታገዳል፡፡ አመልካቾች የመቃወም አቤቱታ ለማቅረብ አቤቱታ በሚያቀርቡበት ንብረት ላይ መብትና ጥቅም ያላቸው ስለመሆኑ

በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ አንቀፅ 33(2) ማስረዳት ያለባቸው ቢሆንም ንብረቶቹ የእኛ ነው ከማለት ውጪ ንብረቶቹ የእነሱ ስለመሆናቸው ያቀረቡት ማስረጃ የለም ንብረቶቹም በተጠሪ ስም ተመዝግበው የሚገኙ ስለመሆኑ በማስረጃ ዝርዝር ላይ ገልፀው አቤቱታቸውን ያቀረቡ በመሆኑ በንብረቶቹ ላይ መብትና ጥቅም የላቸውም ተብሎ የመቃወም አቤቱታቸው ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡

2ኛ ተጠሪ ግንቦት 18 ቀን 2015 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ባቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ሟች ገ/ሚካኤል ከዚህ አለም በ 1972 ዓ.ም የተለዩና አቤቱታው በ 2015 ዓ.ም ከ 43 አመታት በኃላ የቀረበ በመሆኑ በፍ/ብ/ህ አንቀፅ 1000(1) እና (2) መሰረት በይርጋ ቀሪ የተደረገ በመሆኑ አቤቱታው ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ የቃል ክርክር የተደረገ ሲሆን የይርጋ ጊዜን በተመለከተ አመልካቾች ያቀረቡት የመቃወም አቤቱታ ከውርስ ክርክር ጋር የተያያዘ ሳይሆን የመፋለም ክርክር በመሆኑ ባልተጠየቀ ዳኝነት ላይ የቀረበ የይርጋ መቃወሚያ በመሆኑ ውድቅ ሊሆን ይገባል፡፡ መብትና ጥቅም የላቸውም ተብሎ የቀረበውን መቃወሚያ በተመለከተ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት ንብረቱ በአንድ ሰው ተመዝግቦ የሚገኝ መሆኑ ብቻ በቂ አይደለም ንብረቱን በእሽሙር ማህበር በጋራ ሰርተን ያገኘነው ነው በማለት እየተከራከርን በመሆኑ በፍሬ ነገር ክርክር በማስረጃ የሚጣራ እንጂ ከወዲሁ በመቃወሚያ ውድቅ ሊሆን የሚገባ ባለመሆኑ መቃወሚያው ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ክርክር አድርገዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም አመልካቾች ያቀረቡት የመቃወም አቤቱታ የባለቤትነት መብትን መሰረት ያደረገ ክርክር እንጂ ተጠሪዎች የውርስ ሀብት ይዘው ስለሚገኙ የውርስ ሀብቱን እንዲለቁ በማለት የቀረበ ባለመሆኑ የአመልካቾች መብት በይርጋ ይታገዳል ተብሎ የቀረበው መቃወሚያ ውድቅ ተደርጓል፡፡ አመልካቾች የመቃወም አቤቱታ ለማቅረብ መብት የላቸውም ተብሎ የቀረበውን መቃወሚያ በተመለከተ መቃወሚያ የቀረበባቸው ንብረቶች ልዩ የሚንቀሳቀሱ ንብረቶች፣ የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች፣ በ 2ኛ ተጠሪ ስም ያሉ የንግድ ማህበራት የአክስዮን ድርሻዎች፣ በባንክ አካውንት ውስጥ የሚገኙ ገንዘቦች ሲሆኑ እነዚህ ንብረቶችም በ 2ኛ ተጠሪ ስም የተመዘገቡ ስለመሆኑ አመልካቾች ካቀረቡት የመቃወም አቤቱታ እና ተጠሪዎች ካቀረቡት ማስረጃዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ የተጠሪዎች የጋብቻ ውል ተብሎ የቀረበውም የሰነድ ማስረጃ 2ኛ ተጠሪ በውክልና የሚያስተዳድራቸው የቤተሰብ ንብረቶች መሆናቸውን ከጠቀሰ በኃላ ንብረቶቹ የግል ንብረቶች

ስለመሆናቸው ይገልፃል እንጂ በአመልካቾችና በተጠሪዎች ጥረት የተፈራ የጋራ ንብረት ስለመሆኑ የሚያስረዳ አይደለም፡፡ እንዲሁም አመልካቾች የጋራ ንብረቱን የእሽሙር ማህበር በሚመስል መልኩ ሰርተን ያገኘነው ነው ያሉ ቢሆንም የእሽሙር ማህበር በንግድ ህጉም ሆነ በፍ/ብሄር ህጉ አንቀፅ 1258 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሰረት የጋራ ንብረትን ስለማስተዳደርም ሆነ በጋራ ሰርተው ንብረትን ስለማፍራት እውቅና የተሰጠው ግንኙነት አይደለም፡፡ በተጨማሪም አመልካቾች የመቃወም አቤቱታ ያቀረቡባቸው ንብረቶች ባለቤትነት በባህሪው በሰነድ ማስረጃ እንጂ በሰው ምስክር የሚረጋገጡ ባለመሆኑ አመልካቾች የመቃወም አቤቱታ ባቀረቡባቸው ንብረቶች ላይ መብትና ጥቅም ያላቸው ስለመሆኑ ያላስረዱ በመሆኑ ያቀረቡት የመቃወም አቤቱታ ውድቅ ሆኗል በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡

በዚህ ብይን ቅር በመሰኘት አመልካቾች ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 312575 ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ይግባኙ አያስቀርብም በማለት ሰርዞታል፡፡

አመልካች ታህሳስ 15 ቀን 2016 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ ለዚህ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም 2ኛ ተጠሪ አመልካቾች የመቃወም አቤቱታ ባቀረቡባቸው ንብረቶች ላይ መብትና ጥቅም የላቸውም ብለው መቃወሚያ ባላቀረቡበት ሁኔታ ችሎቱ በ 2ኛ ተጠሪ ላይ ክሱ ሊቀጥል ሲገባ መብትና ጥቅም ያላቸው መሆኑን አላስረዱም በማለት የሰጠው ብይን፤ መብትና ጥቅም አለ ወይስ የለም የሚለው የፍሬ ነገር ክርክር በሚደረግበት ጊዜ በማስረጃ ተጣርቶ መሆን ሲገባው ከዚህ በተቃራኒ ህገ መንግስታዊ የመሰማት መብትንና የስነ ስርአት ህጉን በሚጥስ መልኩ የቀረበውን አቤቱታ ውድቅ ማድረጉ፤ የማይንቀቀሳቀስ ንብረትንም ሆነ ልዩ ተንቀሳቃሽን እንዲሁም ሌሎች ንብረቶችን በተመለከተ የሚነሳ ክርክር ማስረዳት የሚቻለዉ በሰነድ ወይም በምዝገባ ብቻ ሳይሆን ንብረቱ የተፈራዉ ወይም የንብረቱን ምንጭ በሌላ መንገድ ስለመሆኑ በማናቸዉም ዓይነት ተቃራኒ ማስረጃ በማስረዳት ነገሩን ማስተባበል እንደሚቻል ከፍ/ሕ/ቁ 1196 ድንጋጌ እና ፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅጽ 9 በሰ/መ/ቁ 88084፣ በቅጽ 15፣ በሰ/መ/ቁ 36320 ላይ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሰጠ በመሆኑ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ብይንና ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊሻር ይገባል በማለት የሰበር አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የቀረበውን የሰበር አቤቱታ ከስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔና ከተገቢው ህግ ጋር አጣምሮ በመመርመር አመልካቾች ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ መነሻ አድርገን መዝገቡን

እንደመረመርነው አመልካቾች የመቃወም አቤቱታ ያቀረቡባቸው ንብረቶች ላይ ያላቸው መብት በሥረ - ነገሩ ክርክር ሳይደረግበትና ማስረጃ ሳይሰማ በንብረቶች ላይ መብት የላቸውም መባሉ ተገቢውን የክርክር ሥርዓት የተከተለ መሆን አለመሆኑ፣ በንብረቶች ላይ የባለቤትነት ማስረጃ መያዝ ባለሀብት እንደሆነ ግምት የሚያስወስድ ቢሆንም ግምቱ በሕግ በተቀመጠው ሥርዓት አግባብ ሊስተባበል የሚችል ከመሆኑ አኳያ ክርክሩና ማስረጃ ሳይሰማ መብት የላቸውም መባሉ የሁሉንም ተከራካሪዎች እኩል የመደመጥ መብት ያከበረና ሕጉን የተከተለ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

ተጠሪዎች መስከረም 30 ቀን 2017 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካቾች መቃወሚያ ባቀረቡባቸው ንብረቶች ላይ መብት ወይም ጥቅም ያላቸው ስለመሆኑ ያቀረቡት ማስረጃ ወይም አሳማኝ ምክንያት የሌለ በመሆኑ ያቀረቡት አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 33(2)፣ 244(2)(መ) እና 245(2) መሠረት ተቀባይት የለውም ተብሎ ክሱ በሥር ፍ/ቤቶች ውድቅ መደረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም፡፡ ተጠሪዎች ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ያቀረብነው መልስ ተመሳሳይ እና ተደጋጋፊ በመሆኑ አመልካቾች 2ኛ ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት አመልካቾች መቃወሚያ ለማቅረብ መብት እና ጥቅም የላቸውም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አላቀረቡም በማለት ያቀረቡት ቅሬታ ተቀባይነት የለውም፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 358 እና 359 መሠረት በሚቀረቡ መቃወሚያዎች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ከቀረበ እና የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያው ህጋዊ ተቀባይነት ካገኘ ፍ/ቤቱ መቃወሚያውን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ ሊያደርግ ይችላል በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ ካደረገው የግድ የሥረ - ነገር ክርክር ማድረግ ግዴታ አይደለም፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆኑት ንብረቶች የማንቀሳቀሱ፣ ልዩ ተንቀሳቃሽ ንብረቶች፣ የንግድ ድርጅቶች፣ የአክስዮን ድርሻ እና በባንክ የተቀመጡ ገንዘቦች በመሆናቸው እነዚህን ንብረቶች ማስረዳት የሚቻለው በሰነድ ማስረጃ እንጂ በሰው ምስክር አይደለም፡፡ አመልካቾች በፍ/ብ/ህ/ቁ 1196 ሥር የተዘረዘሩትን መስፈርቶች አንዱንም አንስተው ባልተከራከሩበት ሁኔታ ይህ ችሎት በራሱ ተነሳሽነት ለተጠሪዎች የተሰጠውን የባለሀብትነት የምስክር ወረቀት በሌላ ማስረጃ ማፍረስ አይቻልም ወይ የሚል ጭብጥ መያዙ ተከራካሪዎች ካቀረቡት ክርክር እና ማስረጃ ውጭ ጭብጥ መያዙ በአግባቡ ባለመሆኑ ጭብጡ ቀሪ ተደርጎ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ብይንና ትዕዛዝ በአግባቡ ነው ተብሎ ሊፀና ይገባል በማለት መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡

አመልካቾች ጥቅምት 13 ቀን 2017 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጥር አጠር ባለመልኩ ከላይ በተዘረዘረው መሰረት የተጠቃለለ በመሆኑ እኛም ለሰበር ቅሬታ መነሻ የሆነውን ፍርድ ከግራ ቀኙ ክርክር፣ ይህ ችሎት ካስቀረበው ጭብጥ አንፃር አመልካቾች መቃወሚያ ለማቅረብ መብትና ጥቅም የላቸውም በማለት መቃወሚያቸው ውድቅ መደረጉ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር አገናዝበን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

መርምረን እንደተረዳነው ከሆነ በስር ፍርድ ቤት አመልካች በተጠሪዎች ላይ ያቀረቡት ዳኝነት ጥያቄ አመልካቾች የክርክሩ ተካፋይ ሳይሆኑ ተጠሪዎች ተከራክረው ያስወሰኑትን ንብረት የተጠሪዎች ባለመሆኑ የተጠሪዎች የጋራ ንብረት ነው ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ቀሪ እንዲሆን በማለት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ አንቀፅ 358 መሰረት መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪዎች አመልካቾች ፍርድን ለመቃወም መብትና ጥቅም የላቸውም ሲሉ በፍተሐብሔር ስነስርዓትሕግ ቁጥር 244 መሰረት ያቀረቤት መቀወሚያ በተመለከተ መብትና ጥቅም ያለመኖራቸው የግራ ቀኙ በኩል ክርክር ከተጠናቀቀ ቦኃላ የሚረጋገጥ ነው እንጅ ከወዲሁ መብትና ጥቅም የላቸውም ተብሎ የመከራከረ መብታቸውን መነፈጋቸው ተገቢ  አይደለም፡፡የስር ፍርድ ቤት ለክርክሩ መነሻ የሆነው ንብረት የማይንቀሳቀስና ልዩ ተንቀሳቃሽ ንብረት በመሆኑ በሰው ማስረጃ የሚረጋገጥ ሳይሆን በሰነድ ማስረጃ የሚረጋገጥ ስለሆነ አመልካቾች ያቀረቡት የማስረጃ ዝርዝር የሰነድ ማስረጃ ሳይሆን የሰው ማስረጃ ዝርዝር በመሆኑ መቃወሚያ ለማቅረብ መብትና ጥቅም የላቸውም በማለት መቃወሚያቸውን ውድቅ አድርጎታል፡፡ አንድ ተከራካሪ ወገን ክስ ለማቅረብ መብትና ጥቅም መኖሩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ አንቀፅ 33(2) መሰረት ካላስረዳ ክሱ ውድቅ ይደረጋል፡፡ መብትና ጥቅም መኖሩ የሚረጋገጠው ክስ ወይም መቃወሚያ ያቀረበው ወገን በሚያቀርበው አቤቱታና በማስረጃ ዝርዝር መሰረት ነው፡፡

የማስረጃ ዝርዝር ሲባል የሰነድ ወይም የሰው ማስረጃ ዝርዝር ሊሆን ይችላል፡፡ ለሚጠየቀው ዳኝነት አግባብነት ያለው ማስረጃ የሰው ማስረጃ ይሁን የሰነድ ማስረጃ ወደፊት የግራ ቀኙ ክርክር ተሰምቶ ከተጠናቀቀ በኃላ ፍርድ ቤቱ የሚወስነው ጉዳይ ነው እንጂ ከወዲሁ የቀረበው ማስረጃ የሰነድ ማስረጃ ባለመሆኑ የማይንቀሳቀስ ንብረት በሰው ማስረጃ ማስረዳት አይቻልም ስለዚህ መቃወሚያ ለማቅረብ መብትና ጥቅም የለቸውም ተብሎ ወደ ድምዳሜ ላይ መድረስ የፍ/ስነስርዓትሕግቁጥር 33 እና 244 ድንጋጌ ያላገናዘበ ነው፡፡፡የማስረጃ አግባብነት የሚመዘነው ወደ ክርክር ውስጥ ከገቡ በኃላ በመጨረሻ በፍርድ ጊዜ የሚታይ ጉዳይ ነው፡፡ ፍርድን የሚቃወምበት ሥርዓት ምን መልክ መያዝ እንዳለበት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ አንቀፅ 359 ስር ይደነግጋል፡፡

የፍርድ መቃወሚያው ክርክር የሚሰማው የመጀመሪያው ክርክር በተሰማበት ስነ ስርአት መሰረት ሆኖ ፍርድ ቤቱ ነገሩን ካጣራ በኃላ መቃወሚያ የቀረበበትን ፍርድ ለማፅደቅ፣ ለማሻሻል ወይም ለመለወጥ ወይም ለመሰረዝ እንደሚችል በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ አንቀፅ 360(2) ስር ይዘረዝራል፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይ የስር ፍርድ ቤት በዚህ በፍ/ብ/ስ/ስ ህግ ቁጥር360(2) ድንጋጌ መሰረት የግራ ቀኙ በኩል ክርክር እና ማስረጃ ተሰምቶ ከተጠናቀቀ በኃላ በመቃወሚያው ላይ ውሳኔ መስጠት ሲገባ ከወዲሁ መቃወሚያ ለማቅረብ አመልካቾች መብት የላቸውም ማለቱ የተከራካሪ ወገኖችን ፍትህ የማግኘትና ክስ የማሰማት ህገ መንግስታዊ መብት የሚጋፋ ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙ ወገን ክስ የማሰማት መብት በእኩል ደረጃ መጠበቅ ይገባዋል፡፡

ሲጠቃለል አመልካቾች ለክርክሩ መነሻ የሆነው የማይንቀሳቀስ እና ልዩ ተንቀሳቃሽ ንብረቶች የተጠሪዎች ሳይሆን የተጠሪዎች የጋራ ንብረታቸው ነው ተብሎ የተሰጠው ፍርድ እንዲሻር በማለት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ አንቀፅ 358 መሰረት ያቀረቡት መቃወሚያ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ አንቀፅ 358 እና ተከታዮቹ ድንጋጌ ተከትሎ ፍርድ መስጠት ሲገባ የስር ፍርድ ቤት ከወዲሁ የግራ ቀኙን ክስና ማስረጃ ሳይሰማ መብትና ጥቅም የላቸውም ብሎ መወሰኑ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 2(4)(ሀ) እና (ለ) እና 10(1)(ለ) መሰረት መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 1ኛ ቤተሰብ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 299251 በቀን 29/12/2013 ዓ.ም የሰጠው ብይን እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ በመዝገብ ቁጥር 312575 በቀን 20/03/2016 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስነስርአት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9(1)(ለ) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በአመልካቾች እና ተጠሪዎች መካከል ያለው ክርክር ወደፊት ማስረጃ ከተሰማ በኃላ የሚረጋገጥ ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤት ማስረጃ ሳይሰማ ከወዲሁ አመልካቾች ፍርድን ለመቃወም መብትና ጥቅም የላቸውም ብሎ መወሰኑ አግባብ ስላልሆነ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ የግራ ቀኙን ማስረጃ ከሰማ በኃላ በህጉ መሰረት ተገቢ የሆነ ፍርድ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በሰበር ስነ ስርአት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9(2) መሰረት መልሰናል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

3. በውሳኔው መሰረት እንዲፈፅም የውሳኔ ግልባጭ ለፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡
4. በዚህ ችሎት የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠ እግድ ካለ ተነስቷል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 256923

የካቲት 24 ቀን 2017ዓ.ም

ዳኞች ፡- ገበየሁ ፈለቀ

ዓለማየሁ ሹናራ

ደረጀ አያና

ኑረዲን ከድር

ብርሃኑ መንግስቱ

አመልካች ፡- ወ/ሮ ሰላማዊት ያደሳ - ከጠበቃ ማሩ ደመላሽ ጋር ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ፀሀዬ ጌታቸው - ቀረቡ

2. ወ/ሮ ገነት ነጋሽ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር እንደባልና ሚስት አብረዉ በኖሩበት ጊዜ ያፈራነዉ ንብረት ነዉ ያሏቸዉን ንብረቶች ለመካፈል ያቀረቡት ክስ አስቀድሞ ዉሳኔ ባገኘ ጉዳይ ለሁለተኛ ጊዜ የቀረበ ክስ ነዉ በሚል ዉድቅ በመደረገ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል በቀረበ የሰበር አቤቱታ መነሻ የተደረገዉን ክርክር የሚመለከት ነዉ፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች በ1ኛ ተጠሪ ላይ በመሰረቱት ክስ የአሁን 2ኛ ተጠሪ ጣልቃ በመግባት የተከራከሩ ሲሆን የክሱ ይዘት በአጭሩ - ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ከቀን 15/04/1999 ዓ.ም ጀምሮ እንደባልና ሚስት አብረን ስንኖር ያፈራነው በአቃቂ ቃሊቲ

ክፍለ ከተማ ወረዳ 08 ክልል ውስጥ የሚገኝ የቤት ቁጥር 121 የይዞታ መለያ ቁጥር AA000070806106 የሆነና በተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ስፋቱ 403 ካሬ ሜትር የሆነ 8 የሚከራዩ ሰርቪስ ቤቶች እና 4 ክፍል ያለው ዋና ቤት እና ቦታ የጋራ ሀብት ስለሆነ ተጠሪ ድርሻዬን እንዲያካፍለኝ በማለት ሌሎች ንብረቶችንም እንደዚሁ በመጥቀስ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

1ኛ ተጠሪ ለክሱ መልስ እንዲሰጡ የታዘዘበት መጥሪያ ቢደርሳቸዉም በጽሁፍ የመከላከያ መልሳቸዉን እንዳላቀረቡ የስር ፍርድ ቤት ብይን ያሳያል፡፡

2ኛ ተጠሪ በክርክሩ ጣልቃ በመግባት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም አመልካች ለአቤቱታቸው መሰረት ያደረጉት ይዞታ በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቃቂ ምድብ 3ኛ የቤተሰብ ችሎት በመ/ቁጥር 71220 ላይ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ንብረት ለመካፈል አቤቱታ አቅርበው ጉዳዩ በሂደት ላይ እንዳለ በቀን 03/11/2010 ዓ.ም በጻፉት አቤቱታ ይዞታው ይገባኛል በማለት አቤቱታ ያቀረብኩት በሌሎች ሰዎች አነሳሽነት ነው፤ይህንን ይዞታ 1ኛ ተጠሪ ከእህቱ በውርስ ያገኘው በመሆኑ የጋራ ሀብት አይደለም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 205 እና 278 መሰረት አመልክተዉ ፍርድ ቤቱም አቤቱታውን ተቀብሎ አፅድቆ መዝገቡን በመዝጋት አሰናብቷቸዋል፡፡ ስለሆነም አስቀድሞ በፍርድ የተወሰነ ጉዳይ ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5 እና 244(2/ለ/ረ) መሰረት መዝገቡ ይዘጋልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካች የጣልቃ ገብ መቃወሚያ ላይ ባሰሙት ክርክር በንብረት ረገድ ከዚህ ቀደም የተደረገ ስምምነትም ሆነ ስምምነት ለማጽደቅ የተሰጠ ትእዛዝ የለም፡፡በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 278 መሰረት ክስ የማንሳት ጉዳይ ከሕገ መንግስቱ አንቀጽ 35/2 ሊታይ ይገባል፡፡ክስ ለማንሳት የተሰጠ ትእዛዝ በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ዉሳኔ እንደተሰጠ ሊቆጠር አይገባም በማለት በሰ/መ/ቁጥር 56795 ላይ የተሰጠዉን የሕግ ትርጉም በመጥቀስ ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን በመ/ቁጥር 90479 ላይ አከራክሮ አስቀድሞ በአመልካችና በ1ኛ ተጠሪ መካከል ክርክር ተደርጎበት የነበረዉን መ/ቁጥር 71220 አስቀርቦ በመመርመር በቀን 09/02/2016ዓ/ም በሰጠዉ ብይን - አስቀድሞ በመ/ቁጥር 71220 ላይ በአመልካችና በ1ኛ ተጠሪ የነበረዉን ክርክር የተመለከተዉ የአቃቂ ቃሊቲ ምድብ 3ኛ ቤተሰብ ችሎት አመልካች የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 205 እና 278 በመጥቀስ ባቀረቡት አቤቱታ መሰረት ክሱ መቋረጡን በመጥቀስ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡የአቤቱታውም ይዘት በአቤቱታው ላይ የጠቀስኩት ቤት 1ኛ ተጠሪ ከእህቱ በውርስ ያገኘው የግሉ ሆኖ ሳለ ሰዎች መካፈል ትችያለሽ ብለው ያሳሳቱኝ ቢሆንም አሁን አብረን የምንኖር እና ልጆችን በጋራ ማሳደግ ስላለብን ቤቱም ይዞታውም የግሉ በመሆኑ ላሳዝነው ስለማልፈልግ እና ይቅር ልለው ስለወሰንኩ በ1ኛ ተጠሪ ላይ ያቀረብኩት ክስ ሙሉ በሙሉ እንዲነሳ እና ስለመነሳቱም ትዕዛዝ እንዲሰጠኝ የሚል ነው፡፡አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ርእሱ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 205 እና 278 በመጥቀስ የቀረበ ቢሆንም ይዘቱ ሲታይ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ቤቱ እና ይዞታው የ1ኛ ተጠሪ የግል ሀብት በመሆኑ ክሱን ትቻለው እንዲቋረጥ የሚል ነው፡፡በአቤቱታው ውስጥ የተጠቀሰው ቤት እና ይዞታ ደግሞ አንድ ብቻ ነው፡፡ስለሆነም በዚህ ተመሳሳይ ንብረት ላይ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በጋራ ያፈራነው ንብረት ነው በማለት ያቀረቡ ሲሆን መዝገቡ ከተዘጋ በኃላ እንደ ባል እና ሚስት ግንኙነት የቀጠሉ ቢሆንም የጋራ የሚያሰብል ሕጋዊ ምክንያት ያላቀረቡ ስለሆነ ከዚህ በፊት በግልፅ ታምኖ ክርክር የተቋረጠበት ጉዳይ እልባት ካገኘ በኂላ በድጋሚ የቀረበ ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5 መሰረት በድጋሚ የቀረበ ክስ ነዉ በማለት ክሱን ዉድቅ በማድረግ ብይን ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 311255 ላይ በበቀን 22/02/16 ዓ.ም በሰጠዉ ብይን ይግባኙን ሰርዞባቸዋል፡፡

አመልካች በቀን 22/04/2016 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ከላይ በተገለፀው መሰረት በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈፅሞበታል በማለት ሲሆን ይዘቱ በአጭሩ፡-ቀደም ሲል በመ/ቁጥር 71220 ክርክር ያደረግንበት ቤት እና ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነው ቤት የቤት ቁጥሩ ተመሳሳይ ከመሆኑ ውጪ በካርታ ቁጥ፣በይዞታ ስፋት፣ይዞታው በተገኘበት አግባብ፣ስሪቱ እንዲሁም የቤቱ ክፍሎች ብዛት ልዩነት ያለው ሲሆን የካርታ ቁጥሩን መመሳሰል ብቻ በመመልከት ክሱ በድጋሚ የቀረበ ነው በሚል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5 መሰረት መዝገቡ መዘጋቱ ስህተት ነው፡፡በመ/ቁጥር 71220 ክርክር ያደረግንበት ስፋቱ 234 ካሬ ሜትር በካርታ ቁጥር 021824 በ1ኛ ተጠሪ ስም ተመዝግቦ የነበረና በ2008 ዓ.ም ለአቶ ወንዲ ደረጀ ቱሉ በሽያጭ የተላለፈ ነባር ይዞታ እና ቤት ነው፡፡በአንፃሩ ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነው ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ስንኖር በ2007 ዓ.ም ከሚመለከተው የመንግስት አካል በይዞታው ላይ መብት ተፈጥሮልን ያገኘነው ስፋቱ 403 ካሬ ሜትር የሆነ ይዞታ መሆኑን በቀን 06/07/2015 ዓ.ም አሻሽዬ ባቀረብኩት የክስ አቤቱታ እና በቀን 26/08/2015 ዓ.ም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 137 መሰረት ተጨማሪ የሰነድ ማስረጃ ለማያያዝ ባቀረብኩት አቤቱታ ላይ ተገልጿል፡፡ቤቱ አንድ አይደለም እንጂ አንድ ነው እንኳን ቢባል ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኛችን በትዳር ለመቀጠል መስማማታችንን በመገንዘብ መዝገቡን ዘጋው እንጂ ንብረትን በሚመለከት የተጀመረውን ክርክር ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ እልባት ለመስጠት በሚያስችል መልኩ የተሰጠ ትዕዛዝ የለም፡፡ጉዳያች የባል እና ሚስት ክርክር በመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 278 ውጤት ከቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 73 እንዲሁም ከሕገ መንግስቱ አንቀጽ 35/2 አንጻር መታየት አለበት፡፡እንዲሁም ለክርክር ምክንያት በሆነው ይዞታ ላይ ከተጠሪ ጋር መዝገቡ ከተዘጋ በኃላ አብረን መኖር ቀጥለን ተጨማሪ ቤቶችን የገነባን በመሆኑ ፍርድ ቤቱ በይዞታው ላይ መሰረታዊ ለውጥ አለ ወይስ የለም የሚለውን ሳያጣራ መዝገቡን በብይን መዝጋቱ ስህተት ስለሆነ ይሻርልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

ችሎቱ የሰበር አቤቱታዉን ከስር ፍርድ ቤቶች የመጨረሻ ዉሳኔ ጋር በማገናዘብ መርምሮ አመልካች በመ/ቁጥር 90479 ላይ በቀን 06/07/2015 ዓ.ም ባቀረቡት አቤቱታ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08 ክልል ውስጥ የሚገኝ በቤት ቁጥር 121፣ በይዞታ መለያ ቁጥር AA000070806106 በተጠሪ ስም

ተመዝግቦ የሚገኝ ስፋቱ 403 ካሬ ሜትር የሆነ 8 የሚከራይ ሰርቪስ ቤቶች እና 4 ክፍል ዋና ቤት ከተጠሪ ጋር የጋራ ሀብታችን በመሆኑ የድርሻዬን እንዲያካፍለኝ የሚል ሲሆን አስቀድሞ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 71220 ላይ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር የነበራቸዉ ክስ ክርክር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 278 መሰረት በፍቃዳቸው እንዲነሳ እንዲፈቀድላቸው በጠየቁት አቤቱታ ላይ የተጠቀሰው የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 የቤት ቁጥር 121 የሆነ 4 ክፍል የሚከራይ 3 ክፍል ቤት የምንኖርበት ቤት የጋራችን በመሆኑ እንድንካፈል በሚል ጠቅሰዉ አቅርበዉ ከነበረዉ ጋር ሲታይ በድጋሚ የቀረበ ነው በሚል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5 መሰረት ውድቅ የተደረገበትን አግባብ ለመመርምር ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ አዝዟል፡፡

1ኛ ተጠሪ በቀን 26/03/2017 ዓ.ም በተጻፈ መልሳቸዉ - አመልካች በመ/ቁጥር 71220 እና በመ/ቁ**ጥር** 90479 አቤቱታ ያቀረቡት በአንድ ቤት ላይ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡እንዲሁም በሁለቱም መዝገቦች የቀረበው ጥያቄ አንድ ዓይነት ነው፡፡ይህ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 ዉስጥ በቤ/ቁጥር 121 ፣በይዞታ መለያ ቁጥር AA000070806106 የሚታወቅ ቤት በውርስ ከእህቴ በ1997 ዓ.ም ያገኘሁት የግል ንብረቴ ስለመሆኑ አመልካች በስር ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 71220 በቀን 03/11/2010 ዓ.ም ባቀረበችው በቃለ-መሐላ በተደገፈ አቤቱታ ያመነችው ጉዳይ ነው፡፡በውርስ ያገኙሁት ይዞታ አጠቃላይ መጠኑ 798.83 ካሬ ሜትር ሲሆን ከዚህ ውስጥ 234 ካሬ ሜትር ኩሽና ብቻ ያለበትን ይዞታ በቀን 04/06/2008 ዓ.ም ለአቶ ወንዲ ደረጀ የተሸጠ እና ከቀሪው 564.83 ካ.ሜ ይዞታ ውስጥ 161.83 ካ.ሜ በመንገድ ልማትና ከአቶ ተስፋዬ ጋዲሳ ጋር በነበረ የፍርድ ቤት ክርክር ከተወሰደ በኂላ የቀረኝ 403 ካ.ሜ ይዞታ እና ይዞታው ላይ ያረፉት ቤቶች ናቸው፡፡ይህንንም ቀሪ የግል የውርስ ንብረቴን በቀን 05/05/2015 ዓ.ም በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት ፊት ቀርቤ ለ2ኛ ተጠሪ ሸጬላቸዋለሁ፡፡አመልካች ክሳቸውን ሲያቋርጡ ወደ ፊት ክስ የማቅረብ መብታቸውን አስጠብቀው አይደለም፡፡አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ በመ/ቁጥር 71220 የነበረው ክርክር ከተዘጋ በኂላ እንደ ባልና ሚስት ግንኙነታችን ቀጥሏል ያሉት ሙሉ ለሙሉ ሀሰት ነው፡፡በመካከላችን እንደ ባልና ሚስት ግንኙነት የለም፡፡ በመሆኑም የተሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊጸና ይገባል በማት ተከራክረዋል፡፡

2ኛ ተጠሪ በቀን 26/03/2017 ዓ.ም ባቀረቡት መልስ - አመልካች በስር ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 71220 በስምምነት በተዘጋው መዝገብ ላይ እና በመ/ቁጥር 90479 ክርክር የተደረገበት ቤትና ቦታ የቤት ቁጥር እና አድራሻ ከመመሳሰል ውጭ የተለያየ ቤት ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር እንዲሁም ከ1ኛ ተጠሪ ጋር የመ/ቁጥር 71220 ላይ በ2010 ዓ.ም ከተዘጋ በኂላ እንደ ባልና ሚስት አብረን ስንኖር በቤቱ ላይ ግንባታ ስላከናወንኩኝ እንደባልና ሚስት አብረን በኖርንበት ጊዜ የተፈራ ሀብት ነው በማለት ያቀረቡት አቤቱታ በሥር ፍርድ ቤት ያላቀረቡትና ያልተከራከሩበት ጉዳይ ነው፡፡ በመ/ቁጥር 71220 ላይ በቀን 03/11/2010

ዓ.ም በስምምነት ክስ ያቋረጥኩበት ቤት በካርታ ቁጥር 021824 በውርስ ለ1ኛ ተጠሪ የተላለፈውን ቤት ነው በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ሀሰት ነው፡፡1ኛ ተጠሪ በካርታ ቁጥር 021824 የሚታወቀውን ቤት በሽያጭ ያስተላለፉት በ2008 ዓ.ም ነው፡፡ይህ ቤት በሽያጭ ስለመተላለፋም አመልካች ያውቃሉ፡፡ስለሆነም አመልካች በመ/ቁጥር 71220 አቤቱታ ያቀረቡበት ቤት በ2008 ዓ.ም ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በስምምነት የሸጡት ቤት ላይ ነው ተብሎ አይገመትም፡፡አመልካች ቦታውን በምን አግባብ እንዳገኙት አልገለጹም፡፡ቤትና ቦታውን በግዥ አግኝተውት ከሆነ የግዥ ውል፤በስጦታ ከሆነ የስጦታ ውል፤በሊዝ ጨረታ ወይም በምሪት አግኝተውት ከሆነ የተመሩበትን ወይም ሌላ ማስረጃ ያላቀረቡ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች በድጋሚ ያቀረቡት ክስ ነዉ በማለት በሰጡት ዉሳኔ የተፈጸመ ስህተት ስለሌላ በማለት ውሳኔው እንዲፀናልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካችም የመልስ መልሳቸውን በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ከላይ አጠር ባለ መልኩ የተገለጸዉ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች እንዲሁም የግራ ቀኙን ክርክር የሚመለከት ሲሆን ይህ ችሎትም ከፍ ሲል የተያዘዉን ጭብጥ መሠረት በማድረግ የአመልካች ክስ አስቀድሞ የመጨረሻ ዉሳኔ ባገኘ ጉዳይ ላይ ለሁለተኛ ጊዜ የቀረበ ነዉ በሚል ዉድቅ በመደረጉ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል ስህተት መፈጸም አለመፈጸሙን እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነዉም የዚህን ችሎት ዉሳኔ የሚሻዉ ነጥብ አመልካች በ1ኛ ተጠሪ ላይ የመሰረቱት ክስ አስቀድሞ በአመልካችና በ1ኛ ተጠሪ መካከል በነበረዉ ክርክር ላይ በተሰጠ ዉሳኔ የመጨረሻ ዉሳኔ ባገኘ ጉዳይ ላይ የቀረበ ክስ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚል ነዉ፡፡ የፍትሐ ብሔር ክርክር አመራር ሥርዓት ዓይነተኛ ዓላማዎች መካከል ዋናዉ ክርክሮች በአነስተኛ ወጪና ምክንያታዊ በሆነ አጭር ጊዜ ፍትሐዊ እልባት የሚያገኙበትን የክርክር ሂደት አመራር ስርዓት መዘርጋት ነዉ፡፡ ይህ ዓላማ ከግብ እንዲደርስ ሕጉ ከሚጠቀምባቸዉ ፖሊሲዎች እና ሥነ ሥርዓታዊ ደንቦች መካከል አንዱ አስቀድሞ የመጨረሻ ዉሳኔ ባገኘ ጉዳይ በድጋሚ ክስ ማቅረብን የሚከለክለዉን ዶክትሪን (Doctrine of Res Judicata) በሕጉ ቁጥር 5 ስር መደንገጉ ነዉ፡፡ በዚህ ድንጋጌ የሥነ ሥርዓት ሕጋችን አካል የሆነዉ አስቀድሞ የመጨረሻ ዉሳኔ ባገኘ ጉዳይ በድጋሚ ክስ ማቅረብን የሚከለክለዉ ዶክትሪን ዓላማዎችም ተከራካሪ ወገኖች ለአላስፈላጊ የጊዜና የወጪ ብክነት ሳይዳረጉ ክርክሮች በአንድ ደረጃ መቋጫ እንዲያገኙ የሚያደርግ (finality) ሥነ ሥርዓት መዘርጋት ፤ የፍርድ ቤቶች የክርክር አመራር በአነስተኛና ምክንያታዊ በሆነ የጊዜ፣የሰዉ እና የገንዘብ ሀብት አጠቃቀም (judicial economy) ተከናዉኖ ወጥነት ያለዉን (consistent) እልባት እንዲያገኝ ማድረግን፤ እንዲሁም ተከራካሪዎች አስቀድሞ ዉሳኔ ባገኘ ጉዳይ ላይ በተደጋጋሚ ክስ በማቅረብ የፍትሐ ብሔር ፍትህ አመራር ሒደቱን ባልተገባ መንገድ እንዳይጠቀሙ (misuse of procedure) መከልከል እንዲችሉ ፍርድ ቤቶች ሂደቱን እንዲቆጣጠሩ ሥልጣን መስጠት፡፡

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5 መሠረት ማንኛዉም በሕግ ሥልጣን የተሰጠዉ ፍርድ ቤት ወይም በሕግ የዳኝነት ስልጣን የተሰጠዉ አካል ክርክሩን ተቀብሎ የመጨረሻ ዉሳኔ የሰጠበት ጉዳይ እና በድጋሚ

የቀረበዉ ክስ ጉዳይ ሲነጻጸር ሁለተኛዉ ክስ *ቀድሞ በፍርድ ከተወሰነዉ ክርክር ሥረ ነገርና ከተያዘዉ ጭብጥ ጋር አንድ ዓይነት ከሆነና በክርክሩ ላይ የነበሩት ወይም ከተከራካሪዎቹ መብት ያገኙት 3ኛ ወገኖች ተመሳሳይ ከሆኑ* በዚያዉ ነገር ላይ ሁለተኛ ክስ ወይም ማናቸዉንም ዓይነት ሌላ ክርክር እንዳይደረግ መከልከል ነዉ፡፡ ስለሆነም ፍርድ ቤቶች ሁለተኛዉ ክስ የተጠቀሱትን የሕጉን መስፈርቶች የሚያሟላ መሆኑን ሲያረጋግጡ ኋለኛዉን ክስ ዉድቅ የሚያደርግ (dismissing of the suit) ዉሳኔ የመስጠት ኃላፊነት ይኖርባቸዋል(የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5፣ 244(2/ለ) እና 245/2 ይመለከቷል)፡፡ ይህ ሰበር ችሎት ከዚህ ድንጋጌ አፈጻጸም ጋር በተያያዘ በሰ/መ/ቁጥር 28522፣ 36780 እና በሌሎች መዛግብት ላይ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5(1 እና 2) ስር በተደነገገዉ መሰረት *ሥረ ነገርና የተያዘዉ ጭብጥ* የሚለዉ ሐረግ አጠቃላይ ይዘቱ ሲታይ *ሥረ ነገር* የሚለዉ በመጀመሪያዉ ክርክር ላይ ለክሱ መሰረት የሆነ ጉዳይ የሚመለከት ወይም ሥረ ነገር - የክሱ መሰረት የሆነዉን ዉል፣ ከዉል ዉጭ፣የይዞታ መብት ወይም ሌላ የንብረት ባለቤትነት ወይም የመብት እና/ወይም የግዴታ ምንጭ… ወዘተ የሚመለከት እንደሆነ የሚያስገነዝብ ነዉ፡፡ *ጭብጥ* በሚል የተገለጸዉ ደግሞ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 246 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መረዳት እንደሚቻለዉ የክስ ምክንያት ወይም የማስረጃ መሰረት ሆኖ በአንደኛዉ ወገን ተገልጾና በዚህ መነሻ ዳኝነት ተጠይቆ በሌላኛዉ ወገን በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የተካደ እና በዚሁ ጭብጥ ላይም ዉሳኔ የተሰጠበት ወይም ሊሰጥበት ይገባ የነበረ የክሱ መሰረት የሆነዉን ሥረ ነገር(ጉዳይ) እና ግራ ቀኙ ተለያይተዉ የተከራከሩበትን የሕግ ወይም የፍሬ ነገር ነጥብ እንደሆነ ለማስገንዘብ ጥቅም ላይ የዋለ ቃል ነዉ፡፡ በድጋሚ በቀረበዉ ክስ እና ቀድሞ ዉሳኔ የተሰጠበት ክስ ሥረ ነገር አንድ አይነት ሆኖ አዲስ የቀረበዉን ክስ በተመለከተ በጭብጥነት ሊመሰረት የሚገባዉ ጭብጥ በቀደመዉ ክርክር የማስረጃ ወይም የመከላከያ መከራከሪያ ሆኖ መቅረብ ይገባዉ የነበረ ወይም መቅረብ ይችል የነበረ ነገር ወይም ምክንያት ከሆነ ከቀድሞዉ ክርክር ጋር ተቀላቅሎ እልባት እንደተሰጠበት የሚቆጠር በመሆኑ አዲስ የቀረበዉ ክስ አስቀድሞ ዉሳኔ በተሰጠበት ጉዳይ በድጋሚ የቀረበ ክስ (res judicata) ነዉ ተብሎ ዉድቅ ሊደረግ እንደሚገባ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5/2 ስር ከተደነገገዉ መረዳት ይቻላል፡፡

ቀደም ሲል በነበረዉ ክርክርና በድጋሚ በቀረበዉ ክርክር ተሳታፊ የሆኑ ወገኖች ተመሳሳይ መሆን አለባቸዉ የሚለዉ ወይም ከእነሱ መብት በተላለፈላቸዉ ወገኖች መካከል የተደረገ ክርክር መሆኑን የሚመለከተዉ በሕጉ አንቀጽ 5/1 የተደነገገዉ መስፈርት በእንግሊዘኛዉ ቅጅ ላይ "…the same parties, or between parties under whom they or any of them claim, litigating under the same title…"ተብሎ የተገለጸ ነዉ፡፡ ይህ የሕጉ መስፈርት ታሳቢ የሚያደርገዉ ፍርድ አስገዳጅነት የሚኖረዉ በተከራካሪዎች ላይ ነዉ የሚለዉን መርህ ሲሆን ተመሳሳይ ተከራካሪዎች ተከራክረዉበት የተሰጠ ዉሳኔ ተከራካሪዎቹን ስለሚያስገድዳቸዉ በድጋሚ በዚያዉ ጉዳይ አዲስ ክስ አቅርበዉ ዉሳኔ እንዲሰጥ የመጠየቅ መብት እንደሌላቸዉ የሚያሳይ ነዉ፡፡ በተለይ

በሕጉ የእንግሊዘኛ ቅጅ ላይ “…litigating under the same title…“ በሚል በግልጽ የተመለከተዉ ሀረግ ደግሞ በተመሳሳይ ዘንግ የተከራከሩ ሰዎች በዚያዉ ጉዳይ ላይ በተመሳሳይ ዘንግ ላይ ሆነዉ አዲስ ክስ ማቅረብ እንደማይችሉ የሚያስገነዝብ እንደሆነ ይህ ሰበር ችሎት በሠ/መ/ቁጥር 229259 ላይ የሠጠዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ያስገነዝባል፡፡

በተጨማሪም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 278/2 ስር በተደነገገዉ መሠረት በፍርድ ቤቱ ፈቃጅነት አዲስ ክስ የማቅረብ መብት ካልተጠበቀለት በስተቀር ማንኛዉም ከሳሽ የሆነ ወገን አቅርቦ የነበረዉን ክስ በሙሉ ወይም በከፊል ካነሳ ወይም ከተወ በኋላ ክስ ባነሳበት ጉዳይ ላይ ሌላ ክስ ሊያቀርብ እንደማይችል ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 278/2 እና 279//1 ጣምራ ንባብ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የጋብቻ ፍቺን ወይም እንደባልና ሚስት የመኖር ግንኙነት መቋረጥን ተከትሎ የንብረት ክፍፍል በተመለከተ የሚቀርበዉን ክርክር ለመወሰን በፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 85 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች እና በሕጉ ሌሎች ክፍሎች ላይ በልዩ ሁኔታ የተደነገጉትን ሥነ ሥርዓታዊ ባህሪይ ያላቸዉን ደንቦች በቀዳሚነት ተፈጻሚ መሆን አለባቸዉ፡፡ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በቤተሰብ ሕጉ ላይ ክስ ስለመተዉ ወይም ከክርክር ዉጭ መሆንን የሚመለከት ልዩ ሥነ ሥርዓታዊ ደንብ የሌለ በመሆኑ ለእንዲህ አይነቱ ክርክርም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 278/2 እና 279/1 ተፈጻሚ ስለሚሆን በግልጽ የንብረት ክፍፍል ተጠይቆበት ክርክር እየተደረገባቸዉ ከሚገኙ ንብረቶች መካከል ያለፍርድ ቤት ፈቃድ በከፊል ወይም በሙሉ ክርክር የተዉ ወይም ያነሳ ተከራካሪ ክርክሩን የተወበትን ወይም ያነሳበትን ያንኑ ንብረት አስመልክቶ ሌላ ክርክር ማቅረብ አይችልም፡፡

ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ አመልካች በ1ኛ ተጠሪ ላይ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቃቂ ምድብ ችሎት በመ/ቁጥር 71220 ላይ በመሰረቱት ክስ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር እንደባልና ሚስት አብረዉ ሲኖሩ ያፈሩት እንደሆነ የገለጹት ይዞታና ቤት በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 ክልል ዉስጥ የሚገኝ የቤት ቁጥሩ 121 የሆነ 4 ክፍል የሚከራይ እና 3 ክፍል የምንኖርበት በሚል የተገለጸ መሆኑን ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡በዚህ መልኩ በክሳቸዉ የገለጹትን አመልካች በቀን 03/11/2010 ዓ/ም በተጻፈ አቤቱታ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር አብረዉ እየኖሩ መሆኑንና ቤትና ቦታዉ ለ1ኛ ተጠሪ የግሉ መሆኑን እንደተረዱ በመግለጽ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 278 መሠረት ክሱን በገዛ ፈቃዳቸዉ ማንሳታቸዉ ታዉቆ ተገቢዉ ትእዛዝ እንዲሰጥላቸዉ ጠይቀዉ ፍርድ ቤቱም ይህንኑ ተቀብሎ መዝገቡን በቀን 05/11/2010ዓ/ም በዋለዉ ችሎት መዝጋቱን መዝገቡ ያሳያል፡፡ከላይ እንደተገለጸዉ አመልካች በመ/ቁጥር 71220 ላይ ክስ የመሰረቱበትን ይዞታ እና ክፍል ቤቶችን በተመለከተ አዲስ ክስ መመስረት አይችሉም፡፡ወደዚህ ድምዳሜ ከመደረሱ በፊት በሁለተኛዉ ክስ ላይ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08 ክልል ውስጥ የሚገኝ የቤት ቁጥር 121 የይዞታ መለያ ቁጥር AA000070806106 የሆነና በተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ስፋቱ 403 ካሬ ሜትር የሆነ 8 የሚከራዩ ሰርቪስ ቤቶች እና 4 ክፍል ያለው ዋና ቤት እና ቦታ በሚል የተገለጸዉ የመሬቱ ስፋት እንዲሁም ክፍል ቤቶቹ ተመሳሳይ መሆን አለመሆናቸዉ፣ መ/ቁጥር 71220 ከተዘጋ በኋላ አመልካችና 1ኛ

ተጠሪ እንደባልና ሚስት አብረዉ ሲኖሩ የተገኘ ይዞታ እና የተሰራ ቤት መኖር አለመኖሩን በአግባቡ በማስረጃ ማጣራት እና ማረጋገጥ ይገባል፡፡በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 244/2 መሰረት በቀረበ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ትክክለኛ ዉሳኔ ለመስጠት ማስረጃ አስቀርቦ መመርመር አስፈላጊ ሲሆን ተገቢዉን ማስረጃ አስቀርቦ መመርመር እንደሚቻል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 245/1 ስር ተደነግጓል፡፡

በተያዘዉም ጉዳይ አመልካች በመ/ቁጥር 71220 ላይ ክስ የመሰረቱበት የመሬት ይዞታ ስፋት እና የቤቶች አይነትና ብዛት አንድ አይነት ነዉ ወይስ አይደለም የሚለዉን በማስረጃ ማረጋገጥ በቀረበዉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ትክክለኛ ዉሳኔ ለመስጠት የግድ አስፈላጊ ነገር ነዉ፡፡ነገር ግን የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በማስረጃ በማጣራት ሳያረጋግጥ በሌላ አነጋገር በሁለቱም መዝገቦች ላይ ዉሳኔ እንዲሰጥበት በክሶቹ የተገለጸዉ የመሬት ይዞታ ስፋትና መሬቶቹ የተገኙበት ጊዜ አንድ አይነት መሆን አለመሆኑን፣ የቤቶቹ ብዛትና አይነት እንዲሁም የተሰሩበት ጊዜ አንድ አይነት መሆን አለመሆኑን በአግባቡ በማስረጃ ሳይረጋገጥ አመልካች ለሁለተኛ ጊዜ ያቀረቡት ክስ ነዉ በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5 መሠረት ክሱን ዉድቅ በማድረግ መወሰኑም ሆነ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህንን ዉሳኔ ማጽናቱ የክርክር አመራር ጉደለት ብቻ ሳይሆን በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40/1 ጥበቃ የተደረገለትን የአመልካችን የንብረት መብት የመጣስ ዉጤት ሊያስከትል የሚችል እንደሆነ ተገንዝበናል፡፡

ሲጠቃለል አመልካች ክስ የመሰረቱበት የመሬት ይዞታ እና ቤቶች አመልካች አስቀድሞ በ1ኛ ተጠሪ ላይ በመ/ቁጥር 71220 ላይ ክስ መስርተዉባቸዉ ከነበረዉ የመሬት ይዞታ ስፋትና መሬቶቹ ከተገኙበት ጊዜ አንጻር ሲታይ አንድ አይነት መሆን አለመሆኑን፣ የቤቶቹ ክፍል ብዛትና አይነት እንዲሁም የተሰሩበት ጊዜ አንድ አይነት መሆን አለመሆኑን በአግባቡ በማስረጃ ሳይረጋገጥ ክሱ ለሁለተኛ ጊዜ የቀረበ ነዉ በሚል ክሱን ዉድቅ በማድረግ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተወስኖ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የጸናዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5 ፣ 278/2 ፣ 279/1 እና 245/1 ስር የተደነገገዉንና ከእነዚህ ድንጋጌዎች አተገባበር ጋር በተያያዘ በዚህ ሰበር ችሎት የተሰጠዉን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሚቃረን በመሆኑ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሀ፣ለ እና ሸ) እና 10(1/ሀ) መሰረት ሊታረም የሚገባዉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 311255 ላይ በቀን 22/02/2016 ዓ.ም የሰጠዉ ብይን እና የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 90479 ላይ በቀን 09/02/2016ዓ/ም የሰጠዉ ብይን በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 መሰረት ተሽረዋል፡፡

2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መዝገቡን በማንቀሳቀስ ከላይ በፍርድ ክፍል በማስረጃ ሊረጋገጡ ይገባል የተባሉ ጭብጦችን በመያዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 245/1 መሰረት በማስረጃ

በማጣራት በ2ኛ ተጠሪ የቀረበዉን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5 ፣ 278/2 እና 279/1 አንጻር በመመርመር ሕግን መሠረት ያደረገ ዉሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩ በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 መሰረት ተመልሶለታል፡፡

3. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ደረጃ ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ተወስኗል፡፡

## ትእዛዝ

1. በዚህ ዉሳኔ መሠረት እንዲፈጽም የዉሳኔዉ ግልባጭ ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ግልባጩ ለግራ ቀኙም ይሰጣቸዉ፡፡
2. በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠ ዕግድ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡
3. ዉሳኔዉ በቀን 05/07/2017ዓ/ም ተነብቦ መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይተላለፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

*የሰ/መ/ቁ 257243*
*የካቲት 26 ቀን 2017ዓ/ም*

ዳኞች ፡- ገበየሁ ፈለቀ

አለማየሁ ሹናራ

ደረጀ አያና

ኑረዲን ከድር

ብርሃኑ መንግስቱ

አመልካች፡- ወ/ሮ ሙርሽዳ ሁሴን

ተጠሪዎች፡- 1ኛ/ ወ/ሮ አልፊያ ሁሴን

2ኛ/ ወ/ሮ ዘቢባ ሁሴን

3ኛ/ ወ/ሮ ጀሚላ ሁሴን

4ኛ/ አቶ ኢድሪስ ሁሴን

5ኛ/ አቶ አብድልሀሚድ ሱልጣን

6ኛ/ መሀመድአሚን ሁሴን

7ኛ/ ወ/ሮ ሲቲ ሁሴን

8ኛ/ ነኢማ ሁሴን

**ማስታወሻ፡** - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

9ኛ/ ራህመት ሁሴን

10ኛ/ ረውዳ ሁሴን

11ኛ/ አሊፍ ሁሴን

12ኛ/ ሳዲያ ሁሴን

13ኛ/ አብድልሀፊዝ ሁሴን

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የውርስ ንብረት እና የሚስትነት ድርሻ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ጉዳዩ በጀመረበት በማእከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች 1ኛ ጣ/ገብ ፤ከ1ኛ እስከ 5ኛ ያሉ ተጠሪዎች ከሳሽ፤ከ6ኛ እስከ 13ኛ ያሉ ተጠሪዎች እንዲሁ ጣ/ገብ አመልካች ነበሩ፡፡ አሁን ከ1ኛ እስከ 5ኛ ያሉ ተጠሪዎች አሁን በክርክሩ በሌሉ ሁለት ተከሳሾች ላይ ባቀረቡት ክስ የሟች አባታቸው አቶ ሁሴን አህመድ ንብረት የሆኑና በሟች ስም የሚገኙ 1ኛ/ በስር 1ኛ ተከሳሽ እጅ የሚገኝ በአሊቾ ውሪሮ ወረዳ ቀረሶ ቀበሌ ገሽዴ ተብሎ በሚጠራ መንደር የሚገኝ 3 ጥማድ የእርሻ መሬት፤2ኛ/ በስር 2ኛ ተከሳሽ እጅ የሚገኝ በወልቂጤ ከተማ 01 ቀበሌ የሚገኝ በ1050 ካ.ሜ ላይ ያለ የንግድ ቤት እና ከቤቱ የሚገኝ የኪራይ ገቢ፤3ኛ/ በስር 1ኛ ተከሳሽ እጅ የሚገኝ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 03-21138 የሆነ ዶልፊን ተሽከርካሪ፤ 4ኛ/ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና በደቡብ ግሎባል ባንክ በሟች ስም በተከፈቱ ሂሳቦች የተቀመጠ ገንዘብ የሟች የውርስ ሀብት ስለሆነ በድርሻችን ተከሳሾች ያካፍሉን ሲሉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁን አመልካች ወደ ክርክሩ ለመግባት ጠይቀው እንዲገቡ ተፈቅዶላቸው ባቀረቡት ክርክር ከሳሾች በክሳቸው ተራ ቁጥር 1 ከገለጹት የገጠር መሬት ላይ 1ኛ ተከሳሽ ለሆነው ለጎጆ መውጫ ከተሠጠው በቁመት 4 ዘንግ ከሆነው ውጪ ያለው አመልካች ግማሽ ድርሻ ያለኝ ስለሆነ የሚስትነት ግማሽ ድርሻዬ እንዲወሰንልኝ፤በተራ ቁጥር 2 የተጠቀሰው ንግድ ቤት ግማሽ ድርሻ የባለቤቴ ስለሆነ 1/4ኛ ድርሻ እንዲወሰንልኝ፤በተራ ቁጥር 3 የተገለጸው ተሽርካሪ የሟች ባለቤቴ ስለሆነ ግማሽ ድርሻ እንዲወሰንልኝ፤ በተራ ቁጥር 4 በተገለጹት ባንኮች ውስጥ የሚገኝ ገንዘብ ግማሹ ድርሻ እንዲወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ከ1ኛ እስከ 5ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱት የአሁን ተጠሪዎች/ በስር ፍ/ቤት ከሳሾች/ አመልካች ባቀረቡት ጥያቄ መሰረት ቢወሰን ተቃውሞ የለንም ያሉ ሲሆን ከ6ኛ እስከ 13ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱት የአሁን

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ተጠሪዎች ደግሞ በተራ ቁጥር 1 ላይ የተጠቀሰው የገጠር መሬት በሟች አባታችን ስም ያለ እና ለ1ኛ ተከሳሽ ለጎጆ መውጫ የተሠጠ ይዞታ የሌለ በመሆኑ አጠቃላይ የውርስ ሀብት ነው ተብሎ በድርሻችን እንዲወሰንልን፤በተራ ቁጥር 2 የተጠቀሰው ንግድ ቤት ሀበይ የገበያ ማእከል በሚል ስያሜ ኀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሆኖ ተመዝግቦ ያለና ግማሹ ድርሻ የ2ኛ ተከሳሽ /አሁን በክርክሩ የሌሉ/ ሲሆን ግማሹ ድርሻ የሟች አባታችን ነው፤ ስለሆነም የግማሹ ድርሻ አክሲዮን በድርሻችን መጠን የትርፍ ክፍፍል እንዲደረግ እንዲወሰንልን፤በተራ ቁጥር 3 የተጠቀሰው ተሽከርካሪም የሟች ውርስ ሀብት በመሆኑ በድርሻችን እንድንካፈል እንዲወሰንልን፤ በተራ ቁጥር 4 በተጠቀሱት ባንኮች ውስጥ ያሉም ገንዘቦች የውርስ ሀብት ስለሆኑ በድርሻችን እንድናገኝ እንዲወሰንልን አመልካች ከሟች ጋር የነበራቸው ጋብቻ ከ31 አመት በፊት በሁኔታ ፈርሷል ተብሎ ፍርድ የተሰጠና፤ ሟች ከ2ኛ ተከሳሽ ጋር የነበረው ጋብቻ በህዳር 25 ቀን 2012 ዓ.ም በፍርድ ቤት ከፈረሰ በኂላ አመልካች ከሟች ጋር በድጋሚ ጋብቻ ስለመፈጸማቸው ያቀረቡት ማስረጃ የለም፡፡ አመልካች ድርሻ መጠየቅ የሚችሉት እንደ አዲስ ጋብቻው ከተቋቋመ በኂላ በጋራ ያፈሩት ንብረት ካለ እንጂ አሁን አቤቱታ ባቀረቡበት ንብረት ላይ የሚገባቸው ንብረት የለም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ በሰጠው ውሳኔ በክሱ ተራ ቁጥር 1ኛ የተጠቀሰው ይዞታ በተመለከተ በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ መሰረት መሬቱን ለመውረስ የሚችለው ከባለይዞታው ጋር በቋሚነት አብረው የሚኖሩ ሰዎች መሆናቸውን፤በዚህም መሰረት የአሁን ከ6ኛ እስከ 13 ያሉ ተጠሪዎች ይዞታው በውርስ ይገባናል የሚሉት ክርክር የህግ ድጋፍ የሌለው መሆኑን፤ከዚህ ይዞታ ውስጥ ለስር 1ኛ ተከሳሽ ለጎጆ መውጫ በሚል የተሰጠው መሆኑን እና የአሁን አመልካችና ከ1ኛ እስከ 5ኛ ያሉ ተጠሪዎች ያመኑ መሆኑን፤ በዚሁም መሰረት ለ1ኛ ተከሳሽ ከተሰጠው ውጭ ያለው ይዞታ ግማሹ የአመልካች ግማሹ ደግሞ የከሳሾች /ከ1ኛ እስከ 5ኛ ያሉ ተጠሪዎች/ ሊካፈሉት የሚገባ ነዉ ፡፡ በክሱ ተራ ቁጥር 2ኛ የተጠቀሰው ሀበይ የንግድ ማእከል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበርን በተመለከተ ሟች ከስር 2ኛ ተከሳሽ ጋር የነበራው ጋብቻ መፍረሱን ተከትሎ በነበራቸው የንብረት ክርክር ግራ ቀኙ በተማመኑበት መሰረት የንግድ ድርጅቱ 50 በመቶ የስር 2ኛ ተከሳሽ መሆኑ እና 50 በመቶው የሟች መሆኑ ተረጋግጦ ለሟች ወራሾች እንዲተላለፍ የአበሽጌ ወረዳ ፍ/ቤት ውሳኔ የሰጠበት መሆኑን፤ የማህበር አባላቱ ሟችና የስር 2ኛ ተከሳሽ መሆናቸው መረጋገጡን፤ የንግድ ማህበሩ ተሸጦ ወራሾች ሊከፋፈሉ የሚችሉበት የህግ አግባብ የሌለ በመሆኑ የሟች ወራሾች የሟች 50 በመቶ የአክሲዮን ድርሻን በየድርሻቸው መጠን ባለአክሲዮን ሊሆኑ ይገባል ያለ ሲሆን አመልካች ከሟች ጋር ቀድሞ የነበራቸው ጋብቻ ከ31 አመት በፊት በሁኔታ ፈርሷል ተብሎ ሀምሌ 15 ቀን 2003 ዓ.ም በፍ/ቤት የተወሰነ እና ድጋሚ ጋብቻ ፈጸሙ የተባለው ከመስከረም 04 ቀን 2012 ዓ.ም በኂላ መሆኑ በመረጋገጡ እና አመልካች በዚህ ንብረት መፈራት ላይ ያደረጉት አስተዋጽ ባለመኖሩ ከአክሲዮኑ ላይ መብት የላቸውም ብሏል፡፡ በተራ ቁጥር 3ኛ የተጠቀሰው ተሽከርካሪን በተመለከተ ደግሞ ሟች ከስር 2ኛ ተከሳሽ ጋር በነበራቸው የጋራ ንብረት ክርክር ለ2ኛ ተከሳሽ ድርሻዋን በመክፈል የግል ያደረጉት መሆኑ በመረጋገጡ ይህ ተሽከርካሪ የሟች ውርስ ሆኖ ወራሾች

የሚከፋፈሉት ነው በማለት  አመልካች አይገባቸውም ብሏል፡፡ በክስ ተራ ቁጥር 4 ላይ የተመለከተው በደቡብ ግሎባል ባንክ እና በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሚገኝ ገንዘብን በተመለከተ ደግሞ ግማሹ የአመልካች ግማሹ ድርሻ ደግሞ የሟች ስለሆነ ግማሽ ድርሻውን የሟች ወራሾች የሚፋፈሉት ነው ሲል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ይግባኝ ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ  በሰጠው ውሳኔ አመልካች አይገባቸውም ከተባለው ንብረት ውስጥ በተራ ቁጥር 3ኛ የተጠቀሰውን ተሸከርካሪ ሟች ለስር 2ኛ ተከሳሽ ባለቤታቸው የዋጋውን ግማሽ ድርሻ ከፍለው ያስቀሩት ከአመልካች ጋር በጋብቻ ውስጥ ባሉበት ጊዜ በመሆኑ በተከፈለው የክፍያ መጠን ላይ መብት ሊጠበቅላቸው ይገባል በማለት ከተሽከርካሪው ላይ አመልካች 1/4ኛ ድርሻ ሊሰጣቸው ይገባል ያለ ሲሆን ሌላው አይገባቸውም የተባለው ንብረት የተፈራው አመልካች ከሟች ጋር ለሁለተኛ ጊዜ ተመልሰው በጋብቻ አብረው መኖር ከመቀጠላቸው በፊት መሆኑ ስለተረጋገጠ አመልካች እነዚህ ንብረቶች አይገባቸውም ተብሎ መወሰኑ የሚነቀፍ አይደለም በማለት የሥር ፍ/ቤቱን ውሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔም ቅር ተሰኝተው ቅሬታቸዉን በሰበር ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ችሎቱ በስር ፍ/ቤቶች በተሰጠዉ ዉሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም በማለት የሰበር ቅሬታዉን በትእዛዝ ዉድቅ አድርጎ መዝገቡን በመዝጋት ግቀኙን አሰናብቷል ፡፡ የሰበር ቅሬታ የቀረበውም በክልሉ በየደረጃው ያሉ ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት ለማሳረም ነው፡፡

የሰበር ቅሬታውም በአጭሩ፡- በአመልካችና በሟች መካከል በ1964 ዓ.ም የተፈጸመው ጋብቻ ከዛሬ 31 አመት በፊት በሁኔታ ፈርሷል ተብሎ በወልቂጤ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በ1987 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በመ/ቁጥር 77/12 ጋብቻ በሁኔታ ፈርሷል ተብሎ ውሳኔ መስጠት ከህገ መንግስት ጋር የሚጸረር ነው በማለት የሰጠውን ውሳኔ የሚጥስ እና የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡ በሟች ስም የሚገኘው በገጠር ያለ መሬት እስካሁን በአመልካች እጅ ያለ መሆኑ እና የመጨረሻዋን ልጇን የወለድኳት በ1988 ዓ.ም በመሆኑ ጋብቻው በሁኔታ ከ31 አመት በፊት ፈርሷል መባሉ የማስረጃ ምዘና ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡ ስለሆነም በ2003 ዓ.ም በወልቂጤ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ ከህገ መንግስቱ ጋር የሚቃረን ስለሆነ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ተብሎ በንግድ ቤቱ ላይ ያለው የሟች የአክሲዮን ድርሻ ላይ እና የተሽከርካሪው ግማሽ ለአመልካች ይገባል ተብሎ እንዲወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር ቅሬታዉን በመመርመር የአሁን የሰበር አመልካች የሟች አቶ ሁሴን መሀመድ የመጀመሪያ ሚስት ሆነዉ በመካከላቸዉ የነበረዉ ጋብቻ በህጋዊ መንገድ ቀሪ ሳይሆን እና የጋራ

ንብረት ክፍፍልም ሳይደረግ ተለያይተዉ ሟች የስር ፍርድ ቤት ሁለተኛ ተከሳሽ የነበሩ ወ/ሮ ዘምዘም አሰፋ የተባሉትን ያገቡ መሆኑን በሟች እና ወ/ሮ ዘምዘም አሰፋ መካከል የነበረዉ ጋብቻ በፍርድ ቤት ዉሳኔ በፍቺ ቀሪ ከሆነ በኋላ አመልካች እና ሟች በድጋሚ በባል እና ሚስትነት አብረዉ ሲኖሩ የነበረ ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ማረጋገጣቸዉን ጠቅሰዋል፡፡ ከዚህ አኳያ ሟች ከወ/ሮ ዘምዘም ጋር ጋብቻ ከመፈጸማቸዉ በፊት የነበሯቸዉ ንብረቶች ፤እንዲሁም ከሁለተኛዉ ጋብቻ በኋላ ያፈሯቸዉ ንብረቶች ተጣርተዉ ባልተለዩበት ሁኔታ የአመልካች የቀደመዉ ጋብቻ በሁኔታ ፍቺ ቀሪ ሆኗል ተብሎ በፍርድ ቤት ተወስኖ ያደረ ነዉ በሚል ምክንያት አመልካች ከአንድ ተሽከርካሪ ዉጪ ሌላ ንብረት ሊካፈሉ አይገባም መባሉ ተገቢነቱን ተጠሪዎች ባሉበት መርምሮ ለማጣራት ያስቀርባል ተብሎ ግራ ቀኙ ተከራክረዉበታል፡፡

ከ1ኛ እስከ 5ኛ ያሉ ተጠሪዎች በጋራ ባቀረቡት መልስ አመልካች በጠየቁት መሰረት ቢወሰንላቸው ተቃውሞ የለንም ብለዋል፡፡ ከ6ኛ እስከ 13ኛ ያሉ ተጠሪዎች በበኩላቸው በጋራ በሰጡት መልስ በአመልካችና በሟች መካከል የነበረው ጋብቻ በሁኔታ ፈርሷል ተብሎ የተሰጠው በ2003 ዓ.ም መሆኑን፤ ውሳኔው የተሰጠው በወቅቱ ተፈጻሚ በነበረው የሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 20938 ከሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ አንጻር ስለመሆኑ፤ ይህ ውሳኔ በይግባኝ ያልተለወጠ ስለመሆኑ፤ የስር የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በአመልካች እና በሟች መካከል የነበረው ጋብቻ በሁኔታ ፈርሷል ሲል የሰጠው አዲስ ውሳኔ አለመኖሩን፤አመልካች ቀድሞ በተሰጠ ውሳኔ ላይ በአዲስ መልክ ክርክር ማቅረብ የማይችሉ መሆኑን፤ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሚሰጣቸው ውሳኔዎች ተፈጻሚነት ያላቸው ከውሳኔው በኋላ ለሚነሱ ጉዳዮች እንጂ አስቀድሞ ውሳኔ ባገኙ ጉዳዮች ላይ አለመሆኑን ጠቅሰው በዚህ ረገድ ያቀረቡት ቅሬታ ውደቅ ይደረግልን ብለዋል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች ሟችና የስር 2ኛ ተከሳሽ በንብረት ላይ ሲከራከሩ ንብረቱ እንደማይገባቸው ስላወቁ ይገባኛል ብለው ያልጠየቁ ስለመሆኑ፤ አመልካች ለክርክር መነሻ የሆነውን ንብረት ለማፍራት አስተዋጽኦ ያልነበራቸው ስለመሆኑ የፍሬ ነገርን ጭብጥ ለመመርመር ስልጣን ባላቸው ፍ/ቤት በማስረጃ ተመዝኖ ውደቅ የተደረገ መሆኑን ጠቅሰው በዚህ ረገድ የቀረበውም የሰበር ቅሬታ ውደቅ ተደርጎ እንድንሰናበት ብለዋል፡፡

የሰበር አመልካችም የሰበር አቤቱታቸዉን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርበዉ ክርክሩ ተጠቃሏል ፡፡ አጠቃላይ የክርክሩ ይዘት እና አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን እኛም የሰበር ቀሬታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ ግራ ቀኙ ካደረጉት ክርክር እንዲሁም ለጉዳዩ አግባብነት ካለዉ ህግ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነዉም የሰበር አመልካች እና የሟች አቶ ሁሴን አህመድ ጋብቻ ሀምሌ 15 ቀን 2003 ዓ.ም በወልቂጤ ከተማ መጀመሪያ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 04261 በተሰጠ ዉሳኔ ፈርሷል ወይስ አልፈረሰም ፈርሷል ከተባለ ያልተካፈሉት የባልን ሚስት የጋራ ንብረት አለ ወይስ የለም የሚሉት ሁለት ጭብጦች ምላሽ ማግኘት ያለባቸዉ ነጥቦች መሆናቸዉን ተገንዝበናል ፡፡

በመሰረቱ የወልቂጤ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰበር አመልካች እና ሟች አቶ ሁሴን አህመድ የነበራቸዉ ጋብቻ ከ30 ዓመታት በላይ ተለያይተዉ ለየብቻቸዉ የኖሩ መሆኑ ስለተረጋገጠ ጋብቻቸዉ በሁኔታ ፍርሷል ሲል ዉሳኔ የሰጠዉ በወቅቱ በነበረዉ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 20938 ላይ ሚያዚያ 11 ቀን 1999 ዓ/ም በተሰጠ አስገዳጅ የሰበር ዉሳኔ መሰረት ሲሆን ይህ የሰበር ችሎት ዉሳኔ በወቅቱ ተፈጻሚ ሲሆን በነበረዉ በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(4) በተሰጠዉ ስልጣን መሰረት በማናቸዉም ፍርድ ቤት አስገዳጅ ዉሰኔ መሆኑ ግልጽ ነዉ ፡፡ በወልቂጤ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተሰጠዉ ዉሳኔ ይግባኝ ተጠይቆበት በበላይ ፍርድ ቤቶች የተሻረ መሆኑን የሚያሳይ ክርክር በሰበር አመልካች በኩል አልቀረበም፡፡ ዉሳኔዉ በበላይ ፍርድ ቤት አስካልተለወጠ ድረስ ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 212 ስር በተደነገገዉ መሠረት ሕጋዊ ዉጤት ያለዉ ዉሳኔ መሆኑ የሚያከራክር ጉዳይ አይደለም ፡፡ የሰበር አመልካች በፌደሬሽን ምክር ቤት በተሰጠ ዉሳኔ ጋብቻ በሁኔታ ሊፈርስ አይገባም ተብሎ ስለተወሰነ የወልቂጤ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተሰጠዉ ዉሳኔ ተፈጻሚነት ያለዉ አይደለም የሚል ይዘት ያለዉ ክርክር አቅርበዋል፡፡ ሆኖም ጋብቻ በሁኔታ አይፈርስም ተብሎ በፌደሬሽን ምክር ቤት ከላይ የተጠቀሰዉን የሰበር ዉሳኔን በመሻር ዉሳኔ የተሰጠዉ በ5ኛ የፓርላማ ዘመን አምስተኛ ዓመት አንደኛ መደበኛ ስብሰባ በመ/ቁ 49/10 ላይ መስከረም 27 ቀን 2012 ዓም ስለሆነ ይህ የፌደሬሽን ምክር ቤት ዉሳኔ ተግባራዊ ሊደረግ የሚገባዉ ዉሳኔ ከተሰጠበት መስከረም 27 ቀን 2012 ዓ/ም ጀምሮ ወደፊት ለሚሰጡ ዉሳኔዎች እንጅ ዘጠኝ አመት ወደ ኋላ በመሄድ በ2003 ዓ/ም የተሰጠን ፍርድ የሚሽር አይሆንም፡፡ ስለሆነም የሰበር አመልካች እና የሟች አቶ ሁሴን አህመድ ጋብቻ ሀምሌ 15 ቀን 2003 ዓ.ም በወልቂጤ ከተማ መጀመሪያ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 04261 በተሰጠ ዉሳኔ ቀሪ የሆነ ነዉ ብለናል፡፡

ሁለተኛዉን ነጥብ በተመለከተ የሰበር አመልካች በግልጽ በሰበር አቤቱታቸዉ ላይ በዚህ ችሎት እንዲወሰንላቸዉ የጠየቁት ዳኝነት በንግድ ቤቱ ላይ ያለዉን የሟች የአክሲዮን ድርሻ እና ዶልፊን መኪና ግመሹን ድርሻ ነዉ ፡፡ በወልቂጤ ከተማ የሚገኘዉ ይህ አመልካች ንግድ ቤት ነዉ በማለት ግማሽ ድርሻ እንዲወሰንላቸዉ የሚጠይቁት ንግድ ቤት የሀበይ የገበያ ማዕከል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሲሆን ይህ ማህበር ራሱን የቻለ ህጋዊ ሰዉነት ያለዉ እና ሁለት አባላት ያሉት ነዉ፡፡ አባላቱም ሟች ሁሴን አህመድ እና የስር ፍርድ ቤት ሁለተኛ ተከሳሽ የነበሩት የሟች ሁሴን አህመድ ሁለተኛ ሚስት ወይዘሮ ዘምዘም አሰፋ እንደሆኑ፤ የተመሰረተዉ በ2009 ዓ/ም እንደሆነ የሰበር አመልካች እና ሟች አቶ ሁሴን አህመድ ጋብቻቸዉ በሁኔታ ፈርሷል ከተባለ በኋላ እንደገና ጋብቻ የፈጸሙት መስከረም 04 ቀን 2012 ዓ/ም መሆኑን አመልካች በዚህ ማህበር ዉስጥ ምንም አይነት አስተዋጽኦ እንደሌላቸዉ መስረጃን የመመርምር እና ፍሬ ነገርን የማጣራት ስልጣን በተሰጣቸዉ የስር በየደረጃዉ ባሉ የክልሉ ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ ፡፡ ዶልፊን መኪናን በተመለከተ ሟች አቶ ሁሴን አህመድ ከቀድሞ ሚስታቸዉ ወ/ሮ ዘምዘም አሰፋ ጋር ፍቺ አድርገዉ የንብረት ክፍፍል ሲፈጽሙ መኪናዉ የቀድሞ ሚስታቸዉ እና

የሚች የጋራ ንብረት ነዉ ተብሎ የፍቺ ዉጤት በሆነዉ የባልና ሚስት ንብረት ክርክር በአበሽጌ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 11529 ቀርቦ በጸደቀ ስምምነት መሰረት ሚች አቶ ሁሴን አህመድ የወ/ሮ ዘምዘም አሰፋን ድርሻ ገንዘቡን በመክፈል መኪናዉን እንዳስቀሩ በስር ፍርድ ቤቶች መረጋገጡን ተረድተናል፡፡

ይህንን መሰረት አድርጎ የስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት መኪናዉ ሚች አቶ ሁሴን አሰፋ የሰበር አመልካችን ከማግባቱ በፊት ከቀድሞ ሚስቱ ጋር ያፈራዉ እና በኋላም በፍቺ ወቅት ያገኘዉ የግል ንብረቱ ስለሆነ የሰበር አመልካችን አይመለከታቸዉም ብሎ ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡

ሆኖም የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በይግባኝ ተመልክቶ ሚች ከወ/ሮ ዘምዘም ጋር የነበረዉ ጋብቻ መፍረሱን ተከትሎ በነበረዉ የንብረት ክፍፍል ክርክር አከራካሪዉን ዶልፊን መኪና የዋጋዉን ግማሽ ሚች ለወ/ሮ ዘምዘም አሰፋ ከፍሎ የግሉ አድርጎ እንዲያስቀር ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ይህንን ተከትሎ በተሰጠ ትዕዛዝ መነሻ የመኪናዉ ግማሽ ዋጋ የተከፈለዉ የወ/ሮ ለምልም አሰፋን በፍቺ መለየት ተከትለዉ ከሚች ጋር ለሁለተኛ ጊዜ ትዳር የመሰረቱት የሠበር አመልካች በጋብቻ ዉስጥ በነበሩበት ጊዜ የተፈጸመ ክፍያ ስለሆነ የሰበር አመልካች ከሚች ጋር በነበሩበት ጊዜ የተፈጸመ ክፍያ ስለሆነ የሰበር አመልካች ሚች ከመኪናዉ ከተካፈሉት ግማሽ ድርሻ ዉስጥ ግማሹ ወይም የመኪናዉ አንድ አራተኛ ድርሻ ይገባቸዋል ሲል ወስኗል፡፡ ይህ ዉሳኔም በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በትዕዛዝ መጽናቱን የተገነዘብን ሲሆን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉን ዉሳኔዎች በማረም ላይ የተገደበ ስለመሆኑ የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80 (3-ሀ) እንዲሁም የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 4 እና 10 ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻል ነዉ፡፡

በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች ማስረጃን መዝነዉ የደረሱበትን የፍሬ ነገር ድምዳሜ ሰበር ሰሚ ችሎት በድጋሚ ሊመረምር የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡

በአዋጅ ቁ.1234/2013 በትርጉም ክፍል አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለዉ አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን፣ ህግ ያላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉን ህግ የሚጠቅስ፣ ለክርክሩ አግባብነት ያለዉ ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለዉ ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፣ በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ዉድቅ በማድረግ የተወሰነ፣ በፍርድ አፈፃፀም ሂደት ከዋናዉ ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትዕዛዝ የተሰጠበት፣ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተወሰነ፣ የአስተዳደር አካል ወይም ተቋም ከህግ ዉጭ የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ በመቃረን የተወሰነ ሲሆን ነዉ፡፡

በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠን ዉሳኔ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታዉን ተቀብሎ በሰበር የማየት ስልጣን የሚኖረዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ የሚቃረን ሲሆን እንዲሁም አግባብነት የሌለዉን ህግ በመጥቀስ ወይም ህግን ያላግባብ በመተርጎም የተሰጠ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን የተሰጠ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሆኖ ጉዳዩም አገራዊ ፋይዳን የሚመለከት ሲሆን ብቻ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 10 (1/ሐ/ እና /መ) ድንጋጌዎች እና ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ/ 208655 የሰጠዉ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ያስገነዝባሉ፡፡ ይህ ትርጉም ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10(2) ድንጋጌ መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ ነው፡፡

ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነ ዉ ሳኔ የተሰጠዉ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስለሆነ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ ይዘት በአዋጁ አንቀጽ 10 (1/ሐ/ እና /መ) ስር የተመለከቱ ድንጋጌዎች አንጻር ሲታይ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሰረታዊ የሆነ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ዉሳኔ

በስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 17369 ግንቦት 25 ቀን 2015 ዓ/ም ተሰጥቶ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 23333 መስከረም 30 ቀን 2016 ዓ/ም ዶለፊን መኪናን በተመለከተ ብቻ ተሻሽሎ የተሰጠዉ ፍርድ እና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 00170 ታህሳስ 09 ቀን 2016 ዓ/ም በትዕዛዝ የጸናዉ ፍርድ መሰረታዊ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም ተብሎ በሰበር ስነ ስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1) መሰረት ጸንቷል፡፡

የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ ተብሏል፡፡

## ትእዛዝ

በሰበር አጣሪ ችሎት ጥር 09 ቀን 2016 ዓ/ም የተሰጠዉ የአፈጻጸም የእግድ ትዕዛዝ ጉዳዩ ዉሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከተዉ ክፍል ፡፡ ይጻፍ ፡፡ ዉሳኔያቸዉ መጽናቱን እንዲያዉቁት የዉሳኔዉ ግላባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍላቸዉ ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መዝገብ ቁጥር - 257774

ቀን - 28/06/2017 ዓ.ም

ዳኞች - ገበየሁ ፈለቀ

ዓለማየሁ ሹናራ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

ብርሃኑ መንግስቱ

አመልካቾች - 1. ወ/ሮ ተናኜ ሞላ ብርሐኔ
2. ወ/ሮ ሃይማኖት ተገኝ ኃይሌ | አልቀረቡም
3. ወ/ሪት ዮርዳኖስ ተገኝ ኃይሌ

ተጠሪ - አቶ ሳሙኤል ተገኝ ኃይሌ - አልቀረቡም

መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው ለምርመራ ስለሆነ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ይህ ጉዳይ የቀረበው አመልካቾች በጥር 10 ቀን 2016 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር ቅሬታ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 239342 በቀን 07/03/2016 ዓ.ም በዋለው ችሎት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሟች አቶ ተገኝ ኃይሌ የተደረገ ኑዛዜ የግልፅ ኑዛዜ ህግ ፎርማሊቲን የማያሟላ ይግባኝ ባይን ክውርስ የሚነቅል ሊፈፀም የማይችል ኑዛዜ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

በመሆኑ ኑዛዜው እንዲፈርስ ሲል የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም በማለት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ አንቀፅ 337 መሰረት የአመልካቾችን ቅሬታ በመሰረዛቸው በዚህ ላይ ቅር በመሰኘታቸው የቀረበ ቅሬታ ነው፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን በስር ፍርድ ቤት አመልካቾች ተጠሪዎች ተጠሪ ደግሞ አመልካች በመሆን ተከራክረዋል፡፡

በስር ፍርድ ቤት ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ ወላጅ አባት ሟች አቶ ኃይሌ ተገኝ የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ኑዛዜ የፈፀሙ መሆኑን አመልካች የሟች ብቸኛ ልጅ መሆኑን ለተጠሪዎች ኑዛዜ በመፈፀም ከሚደርሰው ድርሻ ከሩብ በላይ ጉዳት እንዲደርስበት ያደረገ በመሆኑ ከኑዛዜው እንድነቀል ተደርጊያለሁ ስለዚህ ሟች ፈፀመውታል የተባለው ኑዛዜ እንዲሻርልኝ የሚል ነው፡፡

ከአመልካቾች በኩል የተሰጠው መልስ በአጭሩ ኑዛዜው በህግ ፊት የፀና ነው ሟች ማንም ሰው ሳያስገድዳቸው በራሳቸው ፍቃድና ፍላጎት በትክክለኛ አእምሮ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ ፊት ቀርበው የኑዛዜው ሰነድ ተነቦላቸው በምስክሮች ፊት የቁም ኑዛዜ ያደረጉ ስለሆነ ኑዛዜው ህጋዊ መሆኑን ሟች ጥር 29 ቀን 2012 ዓ.ም ባደረጉት የቁም ኑዛዜ በተራ ቁጥር 2፣ 3 እና 4 የተጠቀሱት የኑዛዜ ተቀባዮች በሟች ስም የሚጠሩ መሆናቸውን ኑዛዜ አድራጊው ልጆች ናቸው ብሎ የተቀበላቸውን ግለሰቦች 3ኛ ወገን ተወላጆች ስላልሆኑ የኑዛዜ ስጦታ ሊበረከትላቸው አይገባም ብሎ መከራከር የሟችን በንብረቱ ላይ የማዘዝ መብትን የሚጥስ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን የኑዛዜ ተቀባዮች ተወላጆች አይደሉም ቢባል እንኳን የኑዛዜ ስጦታ ለተወላጅ ብቻ የሚሰጥ መብት ነው የሚል የህግ ድንጋጌ ያለመኖሩን አመልካች ሟች አባታቸው ባደረጉት ኑዛዜ የኑዛዜ ተቀባይ ነው እንጂ በኑዛዜው ከውርስ አልተነቀለም፡፡ አመልካች ከጠየቁት ዳኝነት አንፃር በኑዛዜው የሚደርሳቸውን ድርሻ በትክክል ለይተው አልጠየቁም የሟች ቁም ኑዛዜ ፈራሽ የሚሆንበት በቂ ምክንያት ስላልቀረበ የአመልካች ክስ ውድቅ እንዲደረግ የሚል ነው፡፡

የግራ ቀኙ የፅሁፍና የቃል ክርክር ከተጠናቀቀ በኃላ ፍርድ ቤቱ ሟች የፈፀመው ኑዛዜ ሊፈርስ ይገባል ወይስ አይገባም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መዝገቡን መርምሮ ሟች በጥር 29 ቀን 2012 ዓ.ም ያደረገው ኑዛዜ በሰነዶች ማረጋገጫ እና ምዝገብ ኤጀንሲ ፊት የተፈፀመ ኑዛዜ መሆኑን፣ ኑዛዜው በግልፅ የሚደረግ ኑዛዜ አይነት መሆኑን፣ በግልፅ የሚደረግ ኑዛዜ በፍ/ብ/ህ አንቀፅ 881 መሰረት መሟላት ያለበት ነጥብ ምን ምን እንደሆነ የተቀመጠ መሆኑን ከዚህ በመነሳት ሟች

የፈፀመው ኑዛዜ በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ኤጀንሲ እና በምስክሮች ፊት የተፈፀመ በመሆኑ ሟች የፈፀሙት ኑዛዜ ህግን የተከተለ የህጉን ፎርማሊቲ ያሟላ በመሆኑ ሊፈርስ አይገባም፡፡ ሟች የፈፀመው ኑዛዜ በ 340 ካ.ሜ ይዞታ ላይ ካለው 170 ካሬ ሜትር ላይ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ በህይወት እስካለች በድርሻቸው እንድትጠቀምበት 1ኛ ተጠሪ ከዚህ አለም በሞት ካረፈች በኃላ አመልካች እና 2ኛ ተጠሪ በጋራ እንዲከፍሉ ሆኖ 3ኛ ተጠሪ አንድ ቤት ሰጥተዋት እንድትጠቀምበት የሚል ይዘት ያለው ኑዛዜ መሆኑን ሟች ኑዛዜ የፈፀመው በሁሉም በሚቀረው ንብረት ላይ በመሆኑ ኑዛዜው አፈፃፀም በክፍያ ደንብ መሰረት የሚከናወን መሆኑን ከውርስ የመንቀል ወይም የክፍያ ማነስ ጉዳይ ሊታይና ሊመረመር የሚገባው ሟች በኑዛዜው ላይ የሚያሰፍረው የንብረት መጠን ከሟች የውርስ ንብረት መጠን ጋር በማመዛዘን የሚታይ በመሆኑ አመልካች ከውርስ ተነቅሏል? ወይስ አልተነቀለም ለማለት ኑዛዜ የተደረገበት አጠቃላይ የሟች ድርሻ ሀብት የዋጋ ግምት ምን ያህል እንደሆነ አልተቀመጠም በይዞታ መጠን ከታየ ኑዛዜው የተደረገው በ 370 ካ.ሜ ይዞታ ላይ ሲሆን ለአመልካችና ለ 2ኛ ተጠሪ ከ 1ኛ ተጠሪ ህልፈት በኃላ እኩል እንዲካፈሉ የሚል በመሆኑ በኑዛዜው መሰረት አመልካች እና 2ኛ ተጠሪ እያንዳንዳቸው የሚደርሳቸው 85 ካሬ ሜትር በመሆኑ አመልካችን ሊደርሰው ከሚችል ድርሻ ከ 1/4ኛ በላይ ጉዳት አልደረሰበትም፡፡ የውርስ ሀብቱን አመልካችና 2ኛ ተጠሪ በስማቸው አድርገው የሚጠቀሙት ከ 1ኛ ተጠሪ ህልፈት በኃላ በመሆኑ የተፈፀመው ኑዛዜ ለመጠቀም የሚያዳግት ባለመሆኑ ሟች ጥር 29 ቀን 2012 ዓ.ም ተፈፀመ የተባለው ኑዛዜ የሚሻርበት አግባብ የለም በማለት የስር አመልካች አቤቱታ ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ቅሬታ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 291662 በቀን 28/2/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት መዝገቡን መርምሮ

1. ጥር 29 ቀን 2012 ዓ.ም ሟች አቶ ተገኝ ኃይሌ አድርገዋል የተባለው ኑዛዜ በፍ/ብ/ህ አንቀፅ 881(1) እና 882 መሰረት በህግ ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው ሰው ፊት ስራውን በሚያካሄድበት ክፍል ያደረገውን የፈረመው ኑዛዜ ነው? ወይስ በሌላ ቦታ ተፅፎ ቀርበው በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ የተመዘገበ ነው?
2. ኑዛዜው በሟች አይደለም ፊርማውም የሟች አይደለም ተብሎ በ 20/05/2014 ዓ.ም ዳኝነት ተጠይቆ እያለ ፍርድ ቤቱ በማስረጃ ሳያጣራ መወሰኑ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም?

3. በቀን 29/09/2014 ዓ.ም የተደረገው የሚች ኑዛዜ ነው ቢባል ከኑዛዜው ይዘት አኳያ ሲታይ ይግባኝ ባይ ውርስ ሀብት ድርሻው ከመጠቀም የሚያግድና ከውርስ እንዲነቀል የሚያደርግ ነው? ወይስ አይደለም?

የሚሉትን ጭብጦችን በመያዝ ሚች የፈፀመው ኑዛዜ በፍ/ብ/ህ አንቀፅ 882 ድንጋጌ አንፃር ሲመዘን ኑዛዜው በህግ ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው ሰው ፊት ስራውን በሚያካሄድበት ክፍል የተደረገ ሚች ኑዛዜ ሲያደርግ የነበረውና ምስክር የሆነው በህግ ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጠው ማን እንደሆነ በኑዛዜው ሰነድ አልተገለፀም በኑዛዜው ሰነድ ላይ በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ኤጀንሲ ቀርቦ የኑዛዜው ሰነድ ተነቦልኝ አድምጬ በሁለት ምስክሮች ፊት የተናዘዝኩት ነው ተብሎ ተፅፎ መገኘቱ ኑዛዜው ውል ለመዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት ስራውን በሚያካሄደው ክፍል የተሰጠ ነው የሚለው የህግ ፎርማሊቲ የሚያሟላ አይሆንም ሊባል የሚገባው ኑዛዜው በሌላ ቀን በሌላ ቦታ ተፅፎ በቀን 29/05/2012 ዓ.ም በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ኤጀንሲ ቀርበው ተነቦ ተመዝግቧል ሊባል ይገባል። ይህ ከሆነ በፍ/ብ/ህ አንቀፅ 881(1) እና (3) መሰረት በ 4 ምስክሮች ፊት የተደረገና የተፈረመ ሊሆን ይገባል። ይህ ያልተፈፀመ በመሆኑ የግልፅ ኑዛዜ ፍርማሊቲ ያሟላ አይደለም። ኑዛዜው ግልፅ ኑዛዜ ፎርማሊቲ ያላሟላ በመሆኑ የሚች ፊርማ መመርመሩ አስፈላጊ አይደለም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር ሚች ጥር 29 ቀን 2012 ዓ.ም ያደረገው ኑዛዜ እንዲፈርስ ሲል ወስኗል።

የአሁን አመልካቾች በዚህ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘታቸው ይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ አንቀፅ 337 መሰረት አያስቀርብም በማለት ሰርዞታል።

የአሁን ሰበር ቅሬታ የቀረበው ይህንን የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት ለማስለወጥ ነው። የሰበር ቅሬታ ይዘቱ በአጭሩ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት የጠየቀው ዳኝነት ኑዛዜው በሚች ያልተደረገ እና ያልተፈረመ እንዲሁም ከንብረቱ ከ 1/4ኛ በላይ የሚያሳጣኝ በመሆኑ ከውርስ ሀብት የሚነቅለኝ ስለሆነ ኑዛዜው እንዲፈርስ የሚል ሆኖ እያለ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያልተጠየቀ ዳኝነት በማንሳት ኑዛዜው ውል ለመዋዋል ስልጣን ያለው ሰው ማን እንደሆነ ኑዛዜ ሰነዱ ላይ አልተገለፀም ኑዛዜው በሌላ ቦታ ተፅፎ ቀርቦ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ የተመዘገበ ነው በማለት ኑዛዜው ፎርማሊቲ አያሟላም ብሎ መሻሩ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው።

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ህ አንቀፅ 882 የሰጠው ትርጉም የህጉን መንፈስ መሰረት ያላደረገና በሰበር መዝገብ ቁጥር 49851 ቅፅ 10 የተሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሚቃረን መሆኑን ኑዛዜው የስጦታ ተቀባዮቹን በመዘርዘር ወደ ስማቸው አዙረው እንዲጠቀሙበት ከገለፀ በኃላ 1ኛ አመልካች በህይወት እስካሉ እንዲጠቀሙበት ሟች በኑዛዜ መፍቀዳቸው የፍ/ብ/ህ አንቀፅ 920 መሰረት ያደረገና የህግ መሰረት ያለው ሆኖ ስለ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ኑዛዜው ወደ ራሷ ስም በማዛወር እንድትጠቀም የሚል አገላለፅ ያለበት በመሆኑ ኑዛዜው ለሚስት የተደረገ ነው ቢባልም ተወላጅን ከውርስ የመንቀል ውጤት ሊያስከትል ይችላል፡፡ ለመፈፀም የማያስችል ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ የፍ/ብ/ህ አንቀፅ 920 እና የሰበር መዝገብ ቁጥር 30991 ቅፅ 7፣ 47622 ቅፅ 22፣ 50901 ቅፅ 10 የሚቃረን በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ እንዲሻርልን የሚል ነው፡፡

ይህ ችሎት ተጠሪ ሟች አባታቸው አቶ ኃይሌ ተገኝ ጥር 29 ቀን 2012 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ እንዲሻር የጠየቁት ኑዛዜ ከሩብ በላይ ጉዳት በማድረስ የሟች ብቸኛ ልጅ ከውርስ ነቅሎኛል በሚል እንጂ ኑዛዜው በህጉ የተመለከተውን ፎርማሊቲ አያሟላም የሚል ባልሆነበት ኑዛዜው ሲደረግ የነበረው በህግ ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጠው ሰው ማን እንደሆነ የሚያመልክት አለመሆኑን ኑዛዜው በኢፌዴሪ ፍትህ ሚኒስቴር የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ ቀርቦ ተነቦልኝ አድምጪ በሁለት ምስክሮች ፊት የተናዘዝኩት ነው ቢልም ኑዛዜው ውል ለማዋዋል ስልጣን ያለው ሰው ስራውን በሚያካሄድበት ክፍል የተሰጠ ነው የሚለውን የህግ ፎርማሊቲ የማያሟላ በሌላ ቀን በሌላ ቦታ ተፅፎ (ተደርጎ) ጥር 29 ቀን 2012 ዓ.ም በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ኤጀንሲ ቀርቦ ተነቧል የሚያሰኝ በመሆኑ አራት ምስክሮች ፊት የተደረገ ስላልሆነ የህጉን መስፈርት አያሟላም መባሉ እንዲሁም በኑዛዜው ላይ የተመለከተውን ቤት እና ይዞታ 1ኛ አመልካች ወደ ስማቸው በማዞር እንዲጠቀሙ መባሉ ሙሉ በሙሉ ንብረቱን የአመልካች ስለሚያደርገው ተጠሪ ከ 1ኛ አመልካች ሞት በኃላ መጠየቅ ስለማይችሉ ተወላጅን ከውር የመንቀል ውጤት አለው የመባሉን አግባብነት በፍ/ብ/ህ አንቀፅ 881፣ 882፣ 917 እና ተከታይ ድንጋጌዎች እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 36777፣ 49851 ላይ ከሰጠው አስገዳጅ ውሳኔዎች አንፃር ለመመርመር ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ የበኩሉን መልስ በ 17/12/2016 ዓ.ም በ 04 ገፅ አቅርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

ፍሬ ነገሩ በአጭሩ ኑዛዜው ፎርማሊቲን ያላሟላ ከውርስ መንቀል ውጤት ያለው ሊፈፀም የማይችል መሆኑን መሰረት በማድረግ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ተጠሪ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማ አያገለግልም!

የጠየቁት ዳኝነት ነው እንጂ ባልተጠየቀ ዳኝነት ላይ የተሰጠ ውሳኔ ባለመሆኑ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡ በስር ፍርድ ቤት 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ከሟች አባቴ ያልተወለዱና የስጋ ዝምድና የላቸውም ተጠሪ የሟች አቶ ኃይሌ ተገኝ ብቸኛ ልጅ ስለሆንኩ 50% ድርሻ በውርስ የሚደርሰኝ ሲሆን አንድ ወላጅ ተወላጅን ከውርስ ያለ ህጋዊ ምክንያት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ሊነቀል እንደማይገባ በፍ/ብ/ህ አንቀፅ 937፣ 938 እና 939 የተደነገገ በመሆኑ ኑዛዜው ተጠሪን በተዘዋዋሪ ከውርስ የነቀለና የአሁኑ አመልካች በህይወት እስካሉ ድረስ ምንም ዓይነት መብትና ጥቅም እንዳላገኝ ያደረገና የገደበ ህገወጥ የሆነ ኑዛዜ በመሆኑ የስር የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ኑዛዜውን በመሻር የሰጠው ውሳኔ በህጉ አግባብ ነው ስለዚህ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ኑዛዜው እንዲፈርስ የሰጠው ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የሌለው ስለሆነ እንዲፀናልኝ የሚል ነው፡፡

አመልካቾች የመልስ መልሳቸውን በ 28/12/2016 ዓ.ም በ 03 ገፅ ሰበር ቅሬታቸውን በማጠናከር አቅርበው ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ በተገለፀው መሰረት በመጠቃለሉ እኛም ለሰበር ቅሬታ መነሻ የሆነውን ፍርድ፣ የግራ ቀኙን ክርክር እና ይህ ችሎት ካስቀረበው ነጥብ፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ኑዛዜው ህጋዊ ፎርማልቲ የማያሟላ እና ተጠሪን ከውርስ ንብረት የመንቀል ውጤት አለው በማለት ኑዛዜው ፈራሽ ነው ሲል የሰጠው ውሳኔ አግባብነት ከፍ/ብ/ህ አንቀፅ 881፣ 882፣ 917 እና ተከታዮች ድንጋጌዎች እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 36777፣ 49851 እና በሌሎች መዝገቦች ላይ ከሰጠው አስገዳጅ ውሳኔዎች አንፃር እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

መርምረን እንደተረዳነው ከሆነ በስር ፍርድ ቤት የተጠሪ ዳኝነት ጥያቄ ሟች አባታቸው አቶ ተገኝ ኃይሌ ጥር 29 ቀን 2012 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ ከሩብ በላይ ጉዳት ያደረሰ በመሆኑ የሟች ብቸኛ ልጅ ከውርስ የነቀለ ስለሆነ ኑዛዜው እንዲሻር የሚል ነው፡፡ ሟች ለአመልካቾችና ተጠሪ በጥር 29 ቀን 2002 ዓ.ም ያደረገው ኑዛዜ ይዘቱ በ 340 ካ.ሜ ቦታ ላይ ካለው ቤት በ 170 ካ.ሜ ይዞታና ቤት ድርሻውን 1ኛ አመልካች ህልፈት ህይወት በኃላ 2ኛ አመልካች እና ተጠሪ እኩል እንዲካፈሉ 3ኛ አመልካች አንድ ክፍል ቤት ብቻ እንዲሰጣት 1ኛ አመልካች የቤቱ ስመ ሀብትነቱን ወደ ስማቸው በማዞር እንዲጠቀሙ የሚል ነው፡፡

የኑዛዜ ፍርማሊቲ በተመለከተ ሟች ኑዛዜው የፈፀመው ሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ኤጀንሲ ፊት ቀርቦ በሁለት ምስክሮች ተረጋግጦ ሟች በነፃነት የተናዘዘና ኑዛዜው ህጋዊ መሆኑ የባለስልጣኑ ባለሞያ አረጋግጦ በሟችና በሁለት ምስክሮች ፊርማ ተረጋግጦ የባለስልጣኑ መ/ቤት ማህተም ተደርጎበት ኮፒው በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ኤጀንሲ ዘንድ እንዲቀመጥ የተደረገ ኑዛዜ መሆኑ ከመዝገቡ ለመረዳት ችለናል፡፡ ኑዛዜው በግልፅ የሚደረግ ኑዛዜ ነው፡፡ በግልፅ የሚደረግ ኑዛዜ መሞላት ያለበት በፍ/ብ/ህ አንቀፅ 881 ስር ተዘርዝሯል፡፡ በፍ/ብ/ህ አንቀፅ 881 ስር በግልፅ የሚደረግ ኑዛዜ በአራት ምስክሮች መረጋገጥ እንዳለበት ሲደነግግ የዚህ ድንጋጌ ልዩ ድንጋጌ የፍ/ብ/ህ አንቀፅ 882 ነው፡፡ በፍ/ብ/ህ 882 ስር በግልፅ ለሚደረገው ኑዛዜ ከምስክሮች መካከል አንዱ ዳኛ ወይም ውል ለመዋዋል ስልጣን የተሰጠው ሰው ሆኖ ኑዛዜውም የተደረገው ይህ ዳኛ ወይም ይህን ለማዋዋል ስልጣን የተሰጠው ሰው ስራቸውን በሚያካሄድበት ክፍል ውስጥ የሆነ እንደሆነ ለኑዛዜው ዋጋ ለማግኘት ሁለት ምስክሮች ብቻ በቂ እንደሆነ ይደነግጋል፡፡

በያዝነው ጉዳይ ኑዛዜው የተደረገው በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ኤጀንሲ ፊት በሁለት ምስክሮች ተረጋግጧል፡፡ ይህ አይነት ኑዛዜ በፍ/ብ/ህ አንቀፅ 882 ስር የሚሸፈን በመሆኑ ኑዛዜውን ያስፈፀመው ባለሞያ ኑዛዜው ትክክለኛ ኑዛዜ እና በሁለት ምስክሮች ፊት ተፈፅሞ ተናዛዡና ሁለት ምስክሮች በፊርማ ያረጋገጡ መሆናቸው በማረጋገጥ ማህተም አሳርፎ ኮፒው በኤጀንሲው እንዲቀመጥ ያደረገ ኑዛዜ ስለሆነ ኑዛዜው በፍ/ብ/ህ አንቀፅ 882 ስር የተዘረዘሩትን መስፈርት የሚያሟላ ሆኖ እያለ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ኑዛዜው በሌላ ቀን በሌላ ቦታ ተፅፎ በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ፅ/ቤት ቀርቦ ሟች ኑዛዜ ተነቦልኝ አድምጬ ፈረምኩ ቢልም ኑዛዜው በፍ/ብ/ህ አንቀፅ 881 መሰረት በአራት ምስክሮች ፊርማ ማረጋገጥ አለበት፡፡

የባለስልጣኑ ባለሞያ ስራውን ያከናወነው ማን እንደሆነ ስሙ አልተገለፀም በማለት ኑዛዜው ፎርማሊቲ ያላሟላ ስለሆነ ፈራሽ ነው ሲል የወሰነበት ሁኔታን ስንመለከት ከመነሻው በኑዛዜ ይዘት ላይ ከግራ ቀኙ በኩል ክርክር አልተነሳም፡፡የኑዛዜ ይዘት ማስረዳት የሚቻለው የኑዛዜውን ጹሑፍ ዋናውን በማቅረብ ወይም ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው ሰው ዘንድ ወይም በፍርድ ቤት መዝገብ ቤት ሹም ትክክለኛ ሆኖ በተመሰከረ አንድ ግልባጭ በማቅረብ እንደሆነ በፍ/ሕ/ቁ 897/1/ ስር ይደነግጋል፡፡የጹሑፍ ማስረጃ ደግሞ በላዩ ላይ የሚገኘው ቃል ሙሉ እምነት የሚጣል በቂ ማስረጃ እንደሆነ በፍ/ሕ/ቁ 2005/1/ ስር ተደንግጎ ይገኛል፡፡

ተጠሪ ኑዛዜው እንዲፈርስ የጠየቀው ኑዛዜው ፎርማለቲ አያሟላም በሚል ሳይሆን ኑዛዜው ከውርስ ድርሻ ከሩብ በላይ ጉዳት ያደረሰ ስለሆነ ነቅሎኛል የሚል ነው፡፡ ተጠሪ ኑዛዜው ፎርማሊቲን አያሟላም ብሎ ባይከራከርም ፍርድ ቤት በራሱ አነሳሺነት ማንሳት እንደሚችል የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የወሰነ በመሆኑ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስለፎርማሊቲ ጉዳይ በራሱ በኩል ማንሳቱ የሚነቀፍ ባይሆንም ኑዛዜው  በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ኤጀንሲ ዘንድ ሟች ቀርቦ በነፃነት የሰጠው ኑዛዜ ሆኖ ሟችም ሆነ ሁለት ምስክሮች በፊርማ ያረጋገጡት ኑዛዜ በመሆኑ ኑዛዜው በፍ/ሕ/ቁ 2005/1/ መሠረት ሙሉ እምነት የሚጣልበት በቂ ማስረጃ ነው፡፡ኑዛዜው በሌላ ቦታ ተጽፎ ስለመምጣቱ በግራ ቀኙ በኩል ክርክር አልተነሳም፡፧የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ኑዛዜው በሌላ ቦታ ተጽፎ የቀረበ ነው በማለት የደረሰው ድምዳሜ ከግምት ያለፈ ሆኖ አላገኘነውም፡፡በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ኤጀንሲ ባለሞያ ስሙ በምስክሮች ስም ዝርዝር ውስጥ አልተገለጸም ስለተባለው ጉዳይ የባለስልጣኑ ሠራተኛ በምስክሮች ስም ዝርዝር ውስጥ

የባለስልጣኑ ሰራተኛ በምስክሮች ስም ዝርዝር መጥቀስ የሚገባው ከባለሞያው ውጭ ሌላ አንድ ምስክር ብቻ በሚሆንበት ጊዜ ነው እንጂ ከባለሞያ ውጭ ሌሎች ሁለት ምስክሮች በሚሆኑበት ጊዜ ባለሞያው ምስክር ሆኖ ለመፈረም አይገደድም ይህንን በተመለከተ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 36777 እና 49851 አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠበት በመሆኑ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለፍ/ብ/ህ አንቀፅ 882 የሰጠው ትርጉም ከሰበር ውሳኔ ጋር የሚጋጭ ነው፡፡ ስለዚህ የሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ኤጀንሲ ባለሞያ ስም በኑዛዜ ውስጥ ያለመጠቀስ ከሰበር መዝገብ ቁጥር 36777 እና 49851 መሠረት ኑዛዜውን ፈራሽ አያደርገውም፡፡

ሌላው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ኑዛዜ ሊሻር ይገባል ብሎ ሲወስን በምክንያትነት የጠቀሰው ሁለተኛው ነጥብ የኑዛዜው ይዘት 1ኛ አመልካች በህይወት እስካለች ንብረቱን ወደ ስማቸው አዛውረው እንዲጠቀሙ የሚል በመሆኑ 1ኛ አመልካች የንብረት ባለቤትነት ወደ ስማቸው ካዞሩ የመሸጥና ለሌላ 3ኛ ወገን የማስተላለፍ መብት ጭምር የሚያስገኝ በመሆኑ ተጠሪን ከውርስ ድርሻ የሚነቅል ነው የሚል ምክንያት ነው፡፡ በእርግጥ የኑዛዜ ይዘቱ ተጠሪ የውርስ ድርሻ ለመጠየቅ የሚችለው 1ኛ አመልካች ከሞቱ በኃላ ነው፡፡ ኑዛዜው በፍ/ብ/ህ አንቀፅ 920 መሰረት ግዴታ ያለበት በፍ/ብ/ህ አንቀፅ 916 መሰረት ደግሞ ገደብ ያለበት ኑዛዜ ነው፡፡ ኑዛዜው የሟች ግላዊ ባህሪይ ያለውና ጥብቅ ነው፡፡ ሟች ንብረቱን በፈለገው መንገድ በስጦታ ወይም በኑዛዜ

የማስተላለፍ ከህግና ህገ መንግስት የመነጨ መብት አለው፡፡ የሚችን ፍላጎት ፍርድ ቤቱ ያለበቂ ምክንያት እንደፈለገው ሊያስቀረው የሚችልበት አግባብ የለውም፡፡

የኑዛዜው ይዘት 1ኛ አመልካች በህይወት እስካሉ ድረስ የንብረት ባለቤትነት በስማቸው በማዞር እንዲጠቀሙ ነገር ግን ከ 1ኛ አመልካች ሞት በኃላ 2ኛ አመልካች እና ተጠሪ እኩል እንዲካፈሉ የሚል ስለሆነ ኑዛዜው ተፈፃሚ የሚሆነውና 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾችና ተጠሪ የውርስ ድርሻቸውን ሊጠየቁ የሚችሉት ከ 1ኛ አመልካች ሞት በኃላ ነው፡፡ 1ኛ አመልካች የንብረት ባለቤትነት ወደ ስማቸው ማዞር ማለት ንብረቱን እንዲሸጡ እና ለሌላ 3ኛ ወገን እንዲያስተላልፉ መብት የሚሰጥ አይደለም፡፡ 1ኛ አመልካች ንብረቱን ወደ ስማቸው ቢያዞሩም ያላቸው መብት እስከ ሚሞቱ ድረስ የአላባ መጠቀም መብት ከሚያስገኝ ውጭ ንብረቱን የመሸጥና የማስተላለፍ ስልጣን የሚሰጥ አይደለም፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ ኑዛዜው ተጠሪን ከውርስ ሀብቱ የሚነቅል ኑዛዜ አይደለም፡፡

ኑዛዜው የኑዛዜ ተጠቃሚውን ወይም ወራሹን ከውርስ ነቅሏል ለማለት የሚቻለው በፍ/ብ/ህ አንቀፅ 1123(1) መሰረት ከውርስ ንብረቱ ውስጥ ከሩብ የበለጠ ጉዳት ከደረሰ ነው፡፡ አሁን በያዝነው ጉዳይ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ንብረት በ 170 ካ.ሜ ይዞታ ላይ ያለው ቤትና ይዞታ ሲሆን የኑዛዜው ይዘት 2ኛ አመልካችና ተጠሪ ከ 1ኛ አመልካች ህልፈት ህይወት በኃላ እኩል እንዲካፈሉ የተባለ በመሆኑ ለአመልካችና ለተጠሪ እኩል (50%) መብት የሚሰጥ ኑዛዜ ስለሆነ ተጠሪን ከውርስ ሀብት የሚነቅል ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በሌላ በኩል የስር ፍርድ ቤት ኑዛዜው ለአፈፃፀም የሚያስቸግር ነው፡፡ ያለበትን ሁኔታ ስንመለከት ኑዛዜው ተፈፃሚ የሚሆነው 1ኛ አመልካች ከሞቱ በኃላ ነው፡፡ 1ኛ አመልካች በህይወት በሚኖሩበት ጊዜ ንብረቱን የመጠቀም መብት አላቸው፡፡ 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾችም ሆነ ተጠሪ የውርስ ሀብት ድርሻ መጠየቅ የሚችሉት 1ኛ አመልካች ከሞቱ በኃላ ነው፡፡ ከ 1ኛ አመልካች ህልፈት ህይወት በኃላ የውርስ ንብረት የመከፋፈል መብት ያላቸው በመሆኑ ኑዛዜው ሊፈፀም የማይችል ኑዛዜ ነው ሊባል አይችልም፡፡

ከዚህ ጋር በተመሳሳይ ጉዳይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 50901 ቅፅ 10 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠ በመሆኑ የስር የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት 1ኛ አመልካች በህይወት እስካለች ንብረቱን ሙሉ በሙሉ ወደ ስማቸው አዙረው እንዲጠቀሙ ማለቱ ተጠሪን ከውርስ ንብረት የነቀለ ኑዛዜ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ ከላይ የተጠቀሰውን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 50901

በቅፅ 10 ላይ የሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉምን የሚጣረስ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡

ሲጠቃለል የተጠሪ ዳኝነት ጥያቄ የሚች አባታቸው አቶ ተገኝ ኃይሌ ያደረጉት ኑዛዜ ከውርስ ሀብት ከሩብ በላይ ጉዳት ያደረሰ በመሆኑ ከውርስ ሀብት የሚነቅለኝ ኑዛዜ ስለሆነ ኑዛዜው እንዲሻር የሚል ሆኖ ሳለ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ኑዛዜው በፍ/ብ/ህ አንቀፅ 881 እና 882 መሰረት ፎርማሊቲ ያሟላ ኑዛዜ አይደለም፡፡ ተጠሪን ከውርስ ሀብት የሚነቅል እና ለአፈፃፀም አስቸጋሪ ኑዛዜ ነው በማለት የሰጠው ፍርድ ኑዛዜው የሚች የግል ባህሪ ያለውና ጥብቅ መሆኑን እንዲሁም ሚች ንብረቱን በነፃነት ለፈለገው ሰው የመናዘዝና የማስተላለፍ ህገ መንግስታዊ መብት ያለው መሆኑን የዘነጋና የተናዛዡን ህገ መንግስታዊ መብት ከመጣሱም ሌላ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 49851፣ 36777፣ 50901 ቅፅ 10 እና 30991 ቅፅ 7 ላይ የተሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉምን የሚጣረስ ነው፡፡ ኑዛዜው የተፈፀመው በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ኤጀንሲ ባለሞያ ፊት በሁለት ምስክሮች ፊት ተናዛዡ ኑዛዜው ተነቦለት አረጋግጦ የፈረመው ኑዛዜ በመሆኑ በፍ/ብ/ህ አንቀፅ 882 መሰረት በሁለት ምስክሮች ፊርማ የተረጋገጠ በመሆኑ ኑዛዜው ፎርማሊቲን ያሟላ ኑዛዜ ነው፡፡

የኑዛዜውን አፈፃፀም በተመለከተ ኑዛዜው ተፈፃሚ የሚሆነው 1ኛ አመልካች ከሞቱ በኃላ ነው፡፡ 1ኛ አመልካች በህይወት እያሉ ንብረቱን ወደ ስማቸው በማዞር የመጠቀም መብት ያጎናፀፈ ኑዛዜ ነው፡፡ ሌሎች አመልካቾችና ተጠሪ የውርስ ድርሻ ሊጠይቁ የሚችሉት 1ኛ አመልካች ከሞቱ በኃላ ነው፡፡ 1ኛ አመልካች ንብረቱን ወደ ስማቸው ቢያዞሩም በንብረት ላይ ከመጠቀም ውጪ የመሸጥና የመለወጥ ስልጣን ያልሰጠ በመሆኑ ንብረቱን ሊሸጡና ሊለውጡ የሚችሉበት አግባብ ባለመኖሩ ኑዛዜው ሌሎች አመልካቾችም ሆነ ተጠሪን ከውርስ ንብረት የሚነቅል አይደለም፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ኑዛዜው ፎርማሊቲን አያሟላም ከውርስ ንብረት ተጠሪን የሚነቅል ነው፡፡ ለአፈፃፀም አስቸጋሪ ነው በማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔን ሽሮ የወሰነው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 49851፣ 36777፣ 30991 እና 50901 ላይ ከተሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሚጣረስ በመሆኑ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 2(4)(ሸ) እና 10(1)(ሀ) መሰረት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ተከታዩ ውሳኔ በአብላጫ ድምፅ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 291662 በቀን 28/02/2015 ዓ.ም የሰጠው ፍርድና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 239342 በቀን 07/03/2016 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስነ ስርአት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9(1)(ለ) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 101265 በቀን 23/07/2014 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስነ ስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9(1)(ሀ) መሰረት ፀንቷል፡፡
3. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡
4. በዚህ ችሎት የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠ እግድ ካለ ተነስቷል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

## የልዩነት ሀሳብ

በ5ኛ ተራ ቁጥር ላይ የተሰየምኩት ዳኛ በሚከተለዉ ምክንያት በአብላጫ ድምጽ ከተሰጠዉ ዉሳኔ በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

ማንኛዉም ሰዉ በመርህ ደረጃ የግል ንብረቱን በፈለገዉ መሠረት በኑዛዜ የማስተላለፍ መብት አለዉ፡፡ ኑዛዜ በባህሪይዉ ተናዛዡ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ ተፈጻሚ የሚሆን መብትና ግዴታ የሚፈጥር ሕጋዊ ተግባር(Juridical act) ነዉ፡፡ሟች አቶ ተገኝ ኃይሌ አድርገዋል የተባለዉ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ኑዛዜ በክሱ የተጠቀሰዉ የዉርስ ሀብት የሆነዉ ቤት ስመ ሀብት በ1ኛ ተጠሪ ስም ዞሮ እንዲመዘገብ የሚፈቅድ ነዉ፡፡ይህም የዉርስ ሀብት የሆነዉ ቤት ባለቤትነት መብት ወደ 1ኛ አመልካች መተላለፉን የሚያሳይ ሁኔታ በኑዛዜዉ መስፈሩን ስለሚያሳይ 1ኛ አመልካች ቤቱን በስማቸዉ ሲያስመዘግቡ ይን በቤቱ ላይ የሚኖራቸዉን ከሁሉ የሰፋ የባለቤትነት መብት መጠቀም ይችላሉ፡፡በዚህ መሠረት የዉርስ ሀብት የሆነዉ ቤት ስመ ሀብት በአሁኑ 1ኛ አመልካች ስም ከተመዘገበ የሟች አቶ ተገኝ ኃይሌ ተወላጅ ወደሆኑት ተጠሪ ሊተላለፍ የሚችለዉ 1ኛ ተጠሪ ከዚህ ዓለም በሞቱ ሲለዩ ብቻ ነዉ፡፡ይህም 1ኛ አመልካች(የሟች ሚስት) ጠቅላላ የዉርስ ሀብት በኔዛዜ ስጦታ እንዲያገኙ የሚያደርጋቸዉ ነዉ(የሕጉ ቁጥር 915/1 ይመለከቷል)፡፡

በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 909/ሐ እና 937 ስር እንደተመለከተዉ ተናዛዡ በመርህ ደረጃ አንድ ወይም ብዙ የሆኑ ወራሾቹን ከወራሽነት መንቀል አሊያም በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 912 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሠረት የሕግ ወራሽ ላልሆኑ ሰዎች ንብረቱን ጠቅላላና ልዩ የኑዛዜ ስጦታ በማድረግ ማስተላለፍ ይችላል፡፡ነገር ግን በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 938 ስር እንደተደነገገዉ ተናዛዡ ከዉርስ ለመንቀል የደረሰበትን ምክንያት በኑዛዜዉ ዉስጥ ካልገለጸ በቀር ልጁን ወይም ወደታች የሚቆጠሩ ተወላጁን ከዉርስ መንቀል አይችልም፡፡
በተጨማሪም በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 915/2 መሠረት ጠቅላላ የኑዛዜ ስጦታ የተደረገለት ሰዉ ስጦታ የተደረገለትን ጠቅላላዉን ዉርስ የመቀበል መብት የሚኖረዉ በኑዛዜ ስጦታ የተደረገላቸዉ ሌሎች ሰዎችና ያለኑዛዜ ወራሾች የሌሉ እንደሆነ ነዉ፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ለክርክሩ መነሻ በሆነዉ ኑዛዝ ሟች ተጠሪን በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 938 መሰረት ምክንያት በመጥቀስ በግልጽ ከዉርስ አልነቀሏቸዉም፡፡ነገር ግን ኑዛዜዉ የተናዛዡን ሞት ተከትሎ ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ የዉርስ ሀብት የሆነዉን ቤት ስመ ሀብት የአሁን 1ኛ አመልካች በስማቸዉ እንዲያስመዘግቡ የሚፈቅድ በመሆኑ ለ1ኛ አመልካች የባለቤትነት መብት የሚያስተላልፍ ስለሆነ ዉጤቱ ተጠሪን ከዉርስ የሚነቅል ነዉ፡፡ስለሆነም የዉርስ ሀብት በሆነዉ የቤቱ ክፍል 1ኛ አመልካች ጠቅላላ የኑዛዜ ስጦታ ተቀባይ ሆነዉ እንዲወርሱ ሊደረግ የሚችለዉ ወይም ኑዛዜዉ ጸንቶ እንዲቀጥል የሚደረገዉ ያለኑዛዜ ወራሽ የሆኑት ተጠሪ ባይኖሩ ነበር፡፡ ስለሆነም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ኑዛዜዉ ተጠሪን የሚነቅል ስለሆነ ፈራሽ ነዉ ሲል የሰጠዉ ዉሳኔም ሆነ ይህንን ዉሳኔ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በትእዛዝ ማጽናቱ ሕግን መሠረት ያደረገ ስለሆነ ከዉጤት አንጻር ሊጸና ይገባል በማለት በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሠ/መ/ቁጥር 258350

የካቲት 28 ቀን 2017 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ገበየሁ ፈለቀ

ደረጀ አያና

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

ብርሃኑ መንግሥቱ

አመልካቾች.....1. ወ/ሮ የሺ አለማየሁ

2. አቶ ሚሊዮን አለሙ

3. አቶ ዮሐንስ አለሙ

4. አቶ ተፈሪ አለሙ

5. አቶ ፀጋዬ አለሙ

6 ወ/ሮ ሔለን አለሙ

7. አቶ ሚኪያስ አለሙ

ተጠሪዎች......1. አቶ መስፍን መኮንን

2. አቶ ስዩም መኩንን

3. አቶ አባተ መኮንን

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

4. ወ/ሮ አይናለም መኮንን

5. ወ/ሮ ታደሰች ማሞ

6. ወ/ሮ አይናበባ መኮንን

7. ወ/ሮ ዮዲት መኮንን

8. አቶ ይምራ መኮንን

9. አቶ አዱኛ መኮንን

10. አልፋ መኮንን

11. ወ/ሪት መቅደስ ጌዲዮን

12. ወ/ሪት ዲና ጌና ጌዲዮን

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የንግድ ማኅበር ለማስፈረስ በሚያስችል ደረጃ በማኅበር አባላት መካከል ብርቱ አለመግባባት ተከስቷል የሚያስብል ምክንያት ምንነትና በማኅበር ህልዉና ላይ የሚኖረዉን ሕጋዊ ዉጤት የሚመለከት ነው፡፡ክርክሩ የተጀመረው በኦሮሚያ ክልል አዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪዎች ከሳሾች አመልካቾች ደግሞ ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስም ቀርቧል፡፡ የመጀመሪያዉ ክስ አጭር ይዘት - የአሁን አመልካቾች የአባታቸው አክሲዮን ተላልፎላቸው የማህበሩ አባል ከሆኑ በኋላ በሕጋዊ መንገድ እንደ አንድ አባል የመብት ጥያቄ ለመጠየቅ በደንቡ የተቀመጠው መስፈርት ካሟሉ ደግሞ የቦርድ አባል ሆነዉ የመመረጥ ሙሉ መብት እያላቸው ከዚህ በተቃራኒ አባታችን ተክተን የቦርድ አባል ካልሆንን በማለት በተለያየ ጊዜ ሁከት እና ረብሻ ሲፈጥሩ ቆይተዋል፡፡ እንደማንኛውም አባል ከማኅበሩ እኩል መብት እያላቸው በሕገ-ወጥ መንገድ በተለያየ ጊዜ ስብሰባ እንዲደረግ ማድረጋቸው፤በሚደረግ ስብሰባ ላይ ሁከት ማንሳት፤የቦርድ አባላት ሥራቸውን በአግባቡ እንዳያከናውኑ ሥራ ቦታ ሄደው ሁከት በመፍጠር በየእለቱ በሚከናወን የማኅበሩ ሥራ ጣልቃ መግባት እና ስብሰባ ተጠርቶ በፍርድ ቤት ቃለ ጉባዔ በማረጋገጥ በአባላት መካከል መልካም ግንኙነት እንዳይኖር እና በጋራ መሥራት እንዳይቻል አድርገዋል፡፡በዚህም ምክንያት ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ መልካም ግንኙነት እና መረዳዳት ስለሌለ ማኅበሩ የተቋቋመበትን ዓላማ ከማሳካት አልፎ በአሁኑ ሰዓት ኪሳራ ውስጥ ገብቷል፡፡ጠቅላላ ጉባዔ ይጠራ በሚል ምክንያት የማኅበሩን ሂሳብ እንዳይንቀሳቀስ የመዝገብ ቁጥር 37258 ላይ በቀን 24/03/2014ዓ/ም ታግዷል፡፡የቦርድ አባል በሆኑት 7ኛ ተጠሪ ላይ በአዳማ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት የወንጀል ክስ በመ/ቁጥር 372940 ላይ እንዲቀርብባቸው አድርገዋል፡፡በመሆኑም በአባላት መካከል ያለው አለመግባባት በጋራ ለመሥራ በማያስችል ደረጃ ላይ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በመድረሱ በስር ፍርድ ቤት 9ኛ ተከሳሽ የነበረው ናዝሬት እና አርሲ ሳሙና እና ዘይት ፋብሪካ ኃ/የተ/የግል ማኅበር የተቋቋመበትን ዓላማ ማስቀጠል ስላልቻለ በንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 አንቀጽ 181/6 መሰረት ማኅበሩ እንዲፈርስ ወይም አመልካቾች ድርሻቸዉን ወስደዉ ከአባልነት እንዲሰናበቱ ይወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አመልካቾች ባቀረቡት መከላከያ መልስ አባታችንን ተክተን እያንዳንዳችን የማኅበሩ አባል ሆነን እንመዝገብ በማለት የመብት ጥያቄ ከመጠየቅ በስተቀር አንድም ቀን የቦርድ አባል እንሁን ብለን ጥያቄ አንስተን አናወቅም፡፡ 8 ሰዎች አንድ ሰው ወክላችሁ እንጂ ሁላችሁም የማኅበሩ አባል መሆን አትችሉም በማለት መብታችንን ስለተጋፉ በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች እስከ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ተከራክረን መብታችንን አስከብረናል፡፡ያነሳነው አንዳችም ሁከትም ሆነ ረብሻ የለም፡፡በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት በየዓመቱ ጠቅላላ ጉባዔ ስላልተካሄደ የማኅበሩን ንብረት በማባከን ለግል ጥቅማቸው በማዋል ላይ ስለሚገኙ ጠቅላላ ጉባዓ ተደርጎ የቦርድ አባል በሕጋዊ መንገድ ተመርጦ የጎደለዉ ይሟላ ብለን የመብት ጥያቄ ብንጠይቅም ፈቃደኛ አልሆኑም፡፡4ኛ፣7ኛ እና 9ኛ ተጠሪዎች የማኅበሩን ንብረት በማባከናቸው ምክንያት በወንጀል ተከሰሱ እንጂ የእኛ ጥፋት አይደለም፡፡ስለሆነም ማኅበሩ የሚፈርስበት እና ከማኅበሩ የምንወጣበት ምክንያት የሌለ ስለሆነ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ በማለት ተከራክረዋል፡፡

በተጨማሪም አመልካቾች በአሁን በ2ኛ፣4ኛ፣7ኛ፣9ኛ፣እና 12ኛ ተጠሪዎች እና በማኅበሩ ላይ በመሰረቱት የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ተከሳሽ ከሳሾች ጠቅላላ ጉባዔ አድርገዉ ምርጫ እንዲደረግ እንዲለወጥ ማድረግ እያለባቸዉ ያለአግባብ የማኅበሩ ንብረት እንዲባክን ሲያደርጉ በመቆየታቸዉ፤ከሳሽ ተከሳሾች የማኅበሩ አባል እንዳይሆኑ በመከልከላቸዉ እና አባል ከሆንን በኋላ ከማኅበሩ የሚገኘዉን ትርፍ ክፍያ ባለማካፈል በከሳሽ ተከሳሾች ላይ ጫና በማድረስ በማኅበሩ ዉስጥ እንቅፋት እንዲፈጠርና ማኅበሩ ሥራዉን እንዳይሰራ በማድረጋቸዉ ከማኅበሩ ላይ ጉዳት ስለደረሰ በንግድ ሕግ አንቀፅ 181/7 መሰረት ከማኅበሩ አባልነት ድርሻቸውን ወስደው እንዲወጡ ይወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪዎች ለተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ በሰጡት መልስ ያለመግባባቱ መንስኤ እና ማኅበሩ ሥራውን እንዲያቆም ምክንያት የሆኑት አመልካቾች እንጂ እኛ አይደለንም፡፡የማኅበሩን ሂሳብ ለማንቀሳቀስ ሥልጣን ያላቸው እንዳያንቀሳቅሱ በማሳገዳቸው የማኅበሩ ሥራ ቆሞ ማኅበሩ ሂሳቡ ላይ ያለው ገንዘብም ለሠራተኛ ደመወዝ ተከፍሎ አልቆ ማኅበሩ ኪሳራ ውስጥ እንዲገባ መነሻ የሆኑት አመልካቾች ስለሆኑ ከማኅበሩ የምንወጣበት ምክንያት የለም፡፡ማኅበሩ እንዲፈርስ ዳኝነት ሳይጠይቁ ከማኅበሩ እንድንወጣ የቀረበው ጥያቄ የሕግ መሰረት የለውም፡፡ የማኅበር ይፍረስ ጥያቄ ሲቀርብ ፍርድ ቤት በንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 አንቀጽ 181/7 መሰረት መርምሮ ውሳኔ መስጠት እንጂ በዚህ ሁኔታ ዳኝነት መጠየቅ ስለማይቻል ክሱ ዉድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃዎችን ሰምቶና መርምሮ በሰጠው ውሳኔ አመልካቾች የማኅበሩ አባል ከመሆን ጋር ተያይዞ ከፍተኛ የሆነ ክርክር እና አለመግባባት የነበረ በመሆኑ በዚህ አለመግባባት ምክንያት በተለያየ ጊዜ በየደረጃዉ ላሉ ፍርድ ቤቶች በወንጀል እና በፍትሐ ብሔር ሲካሰሱ ቆይተዋል፡፡ በግራ ቀኙ አለመግባባት ምክንያት በየአመቱ መደረግ ያለበት ጠቅላላ ጉባዔ ለረዥም አመታት ሳይደረግ ቆይቶ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ጠቅላላ ጉባዔ ሲደረግ እንደነበር ተረጋግጧል፡፡በተጨማሪም የቦርድ አባላት በማኅበሩ የመተዳደሪያ ደንብ መሰረት ጠቅላላ ጉባዔ ሲጠሩ ያልነበሩ መሆናቸውን እና ጠቅላላ ጉባዔ ሲጠራ ደግሞ አመልካቾች ሁከት እየፈጠሩ ከስብሰባ ላይም መቅረታቸውን የስር 9ኛ ተከሳሽ ማኅበር ከ2014 ጀምሮ እስካሁን ድረስ መደበኛ ሥራውን በመሥራት ላይ የማይገኝ ስለመሆኑ በሰው ምስክር እና በሰነድ ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡በዚህም ምክንያት በአሁኑ ጊዜ ማኅበሩ መክሰሩን ግራ ቀኙ አልካዱም፡፡በዚህ ሁኔታ ማኅበሩ የተቋቋመበትን ዓላማ ያሳካል ተብሎ ስለማይገመት በንግድ ሕግ አንቀጽ 181/6 እና 531 መሰረት ፈርሶ በጠቅላላ ጉባዔ አጣሪዎች ተሹመዉ የማኅበሩ ሂሳብ ይጣራ ሲል ወስኗል፡፡እንዲሁም የተከሳሽ ከሳሽነት ክሱን በተመለከተም የስር 9ኛ ተከሳሽ ማኅበር እንዲፈርስ ውሳኔ ስለተሰጠ ሌላዉን የክሱን ፍሬ ነገር መመርመር ባለማስፈለጉ ታልፏል ሲል ወስኗል፡፡

አመልካቾችም በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበዉ ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 434926 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 18/04/2016 ዓ.ም በሠጠዉ ዉሳኔ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ጉድለት የለበትም ሲል አፅንቷል፡፡

አመልካቾች በቀን 21/05/2016 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ከላይ በተገለፀው አግባብ በተሰጠዉ ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት ሲሆን የአቤቱታቸው አጭር ይዘትም - ማኅበሩ መብታችንን ባለመጠበቁ ምክንያት መብታችንን ለማስከበር ፍርድ ቤት መሄዳችን እንደ ፀብ አጫሪነት መወሰዱ ተገቢነት የሌለው ነው፡፡ ያቀረብነው የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ የማኅበሩን አመራሮች ሕገ-ወጥ ሥራ እና ማኅበሩ ዓላማውን እንዳያሳካ መሰናክል መፍጠራቸውን የሚያሳይ እና እነኚህን አመራሮች ከማኅበሩ አባልነት ማስወጣት የሚታይ መፍትሄ ሆኖ ሳለ የስር ፍርድ ቤት ስለዚህ ጉዳይ ምንም ሳይል ማኅበሩ ሥራ ያቆመው በምን ምክንያት መሆኑን በግልጽ የሚታይ ማስረጃ እያለ አለመግባባት በመፈጠሩ እንደቆመ በመውሰድ ችግሩን ወደ አመልካቾች በማምጣት የሰጠው ውሳኔ ተገቢነት የሌለው ነው፡፡በማኅበሩ መክሰር ላይ የቀረበ ክርክር የለም፡፡የመክሰር ውሳኔም አልተሰጠበትም፡፡ይህ በሆነበት ሁኔታ የማኅበሩ አመራሮች በፈፀሙት ወንጀል የሂሳብ ሰነድ ላይ እንዳይፈርሙ የታገዱትን እና ሌላ ሰው ተተክቶ እንዲፈርም ፍቃደኛ ባለመሆናቸው ለጊዜው የቆመ ሆኖ ሳለ መክሰሩ ሳይረጋገጥ ለመፍረሱ ምክንያት መሆኑ የሕግ ስህተት ነው፡፡ስለሆነም ውሳኔው ተሽሮ 4ኛ፣7ኛ፣9ኛ እና 12ኛ ተጠሪዎች ከማኅበሩ አባልነታቸው አክሲዮናቸውን ሸጠው እንዲለቁ ይወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ችሎቱ የሰበር አቤቱታዉንና የመጨረሻዉን ዉሳኔ መርምሮ የስር ፍርድ ቤቶች ለማኅበሩ መፍረስ ምክንያት ተደርገው የተጠቀሱትን ምክንያቶች በመመርመር ማኅበሩ መክሰሩን አረጋግጠዋልን? ተጠሪዎች ማኅበሩ እንዲፈርስ ካቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ አንፃር ውጤቱ ምን ሊሆን ይገባል? በተለያዩ መዝገቦች የቀረቡት የፍትሐ ብሔር ክሶችና በቦርድ አባላቱ ላይ ቀረቧል የተባለው የወንጀል ክስ፣ የማኅበሩ ሂሳብ አለመጣራቱ እነዚህን ተከትሎም ማኅበሩ ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ መደበኛ ሥራውን አለመሥራቱና እንዳይንቀሳቀስ መታገዱ፣ጠቅላላ ጉባዔ በንግድ ሕጉ አንቀፅ 218/2 መሰረት በማኅበርተኞቹ መካከል ብርቱ ጭቅጭቅና አለመስማማት ተፈጥሯል የሚያስብሉ ናቸውን? የሚሉትን ጭብጦች በሰ/መ/ቁጥር 143390፣157305 እና በተመሳሳይ መዝገቦች ከተሰጡት አስገዳጅ የሕግ ትርጉሞች አንፃር ለመመርመር ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ አዝዟል።

1ኛ፣2ኛ፣9ኛ፣እና 10ኛ ተጠሪዎች በቀን 25/11/2016 ዓ.ም በተጻፈ መልሳቸዉ - ከሌሎች ተጠሪዎች ጋር በአንድ ላይ ማኅበሩ እንዲፈርስ ክስ ማቅረባችን የሚካድ ባይሆንም በኋላ ላይ ግን በመካከላችን የነበረውን አለመግባባት ከተራ ጥርጣሬ ያላለፈ እንደሆነ እና በወንጀል ቀርቦ የነበረውም ክስ ሲታይ በሁላችንም መካከል የነበረው አለመግባባት የግንዛቤ ችግር እንጂ ድርጅቱን ለማስፈረስ ተጨባጭ ችግር አለመሆኑን ስላሳየን ከአመልካቾች ጋር ተነጋግረን እርቅ ፈፅመናል። ማኅበሩም እንዳይፈርስ በዚህ መዝገብ ላይ የእርቅ ስምምነታችንን አያይዘናል።በአመልካቾች አቤቱታ የማኅበሩ የቦርድ አባላት በቦርድ አባልነታቸው እንዳይሰሩ ለጊዜው የእግድ ትዕዛዝ የተሰጠ መሆኑ፤የመብት ጥያቄ ማቅረብ እና ወንጀል ተፈጽሟል ብሎ ክስ ማቅረብ መብት በመሆኑ በዚህ ምክንያት መካሰስ ብቻውን ብርቱ ጭቅጭቅ አለ ተብሎ ማኅበሩን ወደ ማፍረስ የሚወስድ ሊሆን አይችልም።አሁን ላይ የማኅበሩን 70 በመቶ አክሲዮን የያዙ የማኅበሩ አባላት መካከል ምንም አይነት ችግር የለም።ማኅበሩ እንዲፈርስ የሚፈልጉ አባላት በማኅበሩ ውስጥ መቀጠል ካልፈለጉ ድርሻቸውን ሸጠው ከማኅበሩ መውጣት እየቻሉ ማኅበሩ እንዲፈርስ መከራከር ተገቢ አይሆንም። የማኅበሩ አባላት ጠቅላላ ጉባዔ ለማድረግ ተገቢውን ምልአተ-ጉባዔ አሟልተው አስፈላጊ ውሳኔዎችን ለማስተላለፍ ተቸግረው አያውቁም።አንድ ማኅበር ከስሯል ለማለት ተገቢው ሂሳብ የማጣራት ሥራ ተሰርቶ፤የማኅበሩ እዳ ከማኅበሩ ካፒታል በላይ ሆኖ ይህም በሂደት የማያገግም መሆኑ ከተረጋገጠ እና ይህም በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ብቻ ነው።አሁን ላይ ግን ማኅበሩ እዳ የሌለበት ሲሆን የማኅበሩ ካፒታል ከግማሽ ቢሊዮን በላይ ነው። ስለሆነም በስር ፍርድ ቤት ማኅበሩ ሥራ በማቆሙ እና የቦርድ አመራሩ ሥራ ላይ ስላልነበሩ እንደ ከሰረ ተደርጎ መቆጠሩ በሥር ፍርድ ቤት ማኅበሩን ለማስፈረስ ከቀረበው ምክንያት ውጪ የሆነ፣ በግራ ቀኙ ያልተነሳ ክርክር እና በማስረጃ ያልተረጋገጠ ነው።እንዲሁም አመልካቾች የማኅበሩን የቦርድ አባላት በማኅበሩ ንብረት ላይ ወንጀል ፈጽመዋል በማለት ክስ አቅርበው መታሰራቸው በዉጤት ደረጃ ትክክል ባይሆንም ይህ ማኅበር ለማስፈረስ በቂ ምክንያት ሊሆን አይችልም ሲሉ ተከራክረዋል።

በሌላ በኩል 4ኛ፣5ኛ፣6ኛ፣7ኛ፣8ኛ እና 12ኛ ተጠሪዎች በቀን 17/12/2016 ዓ.ም በጋራ በተጻፈ መልሳቸዉ እንዲሁም 11ኛ ተጠሪ በቀን 23/03/2017 ዓ.ም በተናጠል በተጻፈ መልሳቸዉ - የአመልካቾችን አቤቱታ ከተሻረው የንግድ ሕግ ድንጋጌ አንፃር መመርመሩ እና የተሻረውን የንግድ ሕግ መሠረት ተደርጎ ከተሰጡት የሰበር ውሳኔዎች አንፃር ጭብጥ መያዙ አግባብነት የለውም፡፡ተጠሪዎች ክሱን ያቀረብነው በአዲሱ የንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 አንቀፅ 181(4፣ 6 እና 7) መሰረት የንግድ ማኀበር ስለሚፈርስበት ሁኔታ በሚደነግገው መሠረት ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም በማኀበሩ አባላት መካከል ብርቱ አለመግባባት መኖሩን አረጋግጦ ይህ ደግሞ ማኀበሩ የተመሰረተበትን ዓላማ ከግብ እንዳያደርስ ያደረገ ስለሆነ ማኀበሩ መፍረስ አለበት በማለት ወስኗል፡፡ስለሆነም በግራ ቀኙ መካከል ያለው ክርክር ከዘጠኝ አመት በላይ ለሚሆን ጊዜ የቆየ መሆኑና ማኀበሩ ላለፉት 3 ዓመታት ተዘግቶ ያለ አንዳች ሥራ መቆየቱ እንዲሁም በአሁኑ ጊዜ የማኀበሩ ካፒታል አልቆ ንብረቶች በእዳ እየተሸጡ መሆናቸው በስር ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር በማስረጃ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ስለሆነ እና ይህ ደግሞ ለክሱ መሠረት ተደርጎ የቀረበበትን የሕግ ድንጋጌ የሚያሟላ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች በዚህ ረገድ የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም፡፡ማኀበሩ እንዲፈርስ የተሰጠው ውሳኔ በንግድ ሕጉ መሠረት ብርቱ ጭቅጭቅና አለመግባባት በማኀበረተኞቹ መካከል መኖሩ ተረጋግጦ ነው፡፡የተፈጠረውም አለመግባባት የአንድ ጊዜ ክስተት ሳይሆን 1ኛ) ከ2007 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በተለያዩ አስር መዛግብት ላይ የፍትሐ ብሔርና የወንጀል ክርክር በመካከላቸዉ መኖሩ፤2) በዚህ መልኩ በመካከላቸዉ ባለዉ ክርክር ምክንያት ይህ ማኀበር ከ2012 ዓ/ም ጀምሮ ሥራዉን አስፈላጊ በሆነ ሁኔታ ሲሰራ ያልነበረ መሆኑ፤3) ከ2014ዓ/ም ህዳር ወር ጀምሮ አመልካቾች የማኀበሩን ገንዘብ ለማንቀሳቀስ ሥልጣን ያላቸዉ ሰዎች እንዳያንቀሳቅሱ እግድ በማሰጠታቸዉ ምክንያት ማኀበሩ ከ3 ዓመት በላይ ለሆነ ጊዜ ሥራ አቁሞ የተዘጋ መሆኑ፤4) የድርጅቱ ሠራተኞች ያለአንዳች ሥራ ከሦስት ዓመት በላይ ለሆነ ጊዜ በፍርድ ቤት ክስ በማቅረብ ዉሳኔ እያሰጡ በማኀበሩ የባንክ ሂሳብ ላይ ያለዉን ገንዘብ ሲወስዱ የነበሩ በመሆኑ ማኀበሩ ካፒታሉን ሙሉ በሙሉ የጨረሰ በመሆኑ፤ 5) ለምርት በዉጪ አገር ምንዛሬ የገቡ ጥሬ እቃዎች የቆይታ ጊዜአቸዉ አልፎ ከሥራ ዉጭ በመሆናቸዉ እነዚህም ምክንያቶች ለማኀበሩ መፍረስ እንደ በቂ ምክንያት የሚወሰዱ ስለሆኑ ውሳኔው እንዲፀናልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

3ኛ ተጠሪ በመጥሪያ ጥሪ ተደርጎላቸዉ ባለመቅረባቸዉ መልስ የመስጠት መብታቸዉ ታልፏል፡፡ አመልካቾችም የመልስ መልሳቸውን በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ከላይ አጠር ባለ መልኩ የተገለጸዉ የግራ ቀኙን ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት የሚመለከት ሲሆን እኛም ከፍ ሲል የተያዙትን ጭብጦች መሠረት በማድረግ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ የንግድ ማኀበር እንዲፈርስ የተወሰነዉ የማኀበሩ ዓላማ ከግብ እንዳይደርስ የሚያስተጓጉል ብርቱ አለመግባባት በማኀበሩ አባላት መካከል መከሰቱ ተረጋግጦ ነዉ ወይ? ሕጉ በሚጠይቀዉ ልክ ማኀበሩን

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ሊያስፈርስ የሚችል በቂ ምክንያት አልተከሰተም የሚባል ከሆነ ክርክሩ እልባት ማግኘት ያለበት በምን አግባብ ሊሆን ይገባል? የሚሉ ጥቅል ጭብጦችን በመያዝ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል መሰረታዊ የሕግ ስህተት መፈጸም አለመፈጸሙን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

በመጀመሪያም ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ የንግድ ማኅበር እንዲፈርስ የተወሰነዉ የማኅበሩ ዓላማ ከግብ እንዳይደርስ የሚያስተጓጉል ብርቱ አለመግባባት በማኅበሩ አባላት መካከል መከሰቱ ተረጋግጦ ነዉ ወይ? በሚል የተያዘዉን ጭብጥ መርምረናል፡፡የንግድ ማኅበራት ለአገር፣ ለማኅበረተኞቹም ሆነ ለጠቅላላዉ ኅብረተሰብ በርካታ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጥቅሞችን እንደሚያስገኙ ይታወቃል፡፡ለአብነት የንግድ ማኅበራት የሚያበረክቱትን ዋና ዋና ጥቅሞች ለመጥቀስ ያህል በኢኮኖሚ ረገድ - በርካታ የሥራ እድል በመፍጠር የሥራ አጥነት ችግር ይቀርፋሉ፤ የእቃዎችና የአገልግሎት ዘርፍ ምርታማነትን በማሳደግ አገራዊ የምርት መጠን ያሳድጋሉ፤ ዉጤታማ ምርትና ምርታማነት እንዲኖር በማድረግ የአቅርቦትና የፍላጎት መጠን እንዲቀራረብ ያደርጋሉ፤ኢኮኖሚ ያነቃቃሉ፤በምርምር ሥራ ላይ በሚያደርጉት ኢንቨስትመት አዳዲስ ግኝቶች እንዲፈጠሩና የቴክኖሎጂ ዉጤቶች እንዲበለጽጉ በማድረግ የኑሮ ዉጣዉረድ እንዲቀል ያደርጋሉ፤መንግሥት ለጠቅላላዉ ኅብረተሰብ የሚሆኑ መሠረተ ልማቶችን፣ትምህርት ቤቶችን፣ የጤና ተቋማትንና ሌሎች መንግሥታዊ ተግባራትን የሚያከናዉንበትን ከፍተኛ ግብር ከሚያገኙት ትርፍ ላይ ይከፍላሉ፡፡ ከማኅበራዊ ጠቀሜታ አንጻርም - በራሳቸዉ አነሳሽነት ከሚያገኙት ትርፍ ቀንሰዉ በጀት መድበዉ ማኅበራዊ አገልግሎቶች እንደ ትምህርት፣ጤና እና የኅብረተሰቡ የኑሮ ሁኔታ በሚያሻሽሉ ጉዳዮች ላይ በመሳተፍ ማኅበራዊ ኃላፊነታቸዉን(Corporate Social Reisponsiblity) ይወጣሉ፤ የዕቃዎችና የአገልግሎት ምርታማነት እንዲጨምር በማድረግ የኅብረተሰቡ የአኗኗር ሁኔታ እንዲሻሻልና ድህነት እንዲቀንስ ማድረግ የሚሉትን እና ሌሎች ጠቃሚ ማኅበራዊ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡

ግራ ቀኙ አባል የሆኑበትና እንዲፈርስ የተወሰነበት የንግድ ማኅበር ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር እንደሆነ ከክርክሩ ተገንዝበናል፡፡ ይህ የንግድ ማኅበር የተቋቋመዉ በ1952 የወጣዉ የንግድ ሕግ ተፈጻሚ ሲሆን በነበረበት ጊዜ እንደሆነ ክርክሩ የሚያሳይ ቢሆንም ማኅበሩ እንዲፈርስ ዳኝነት ተጠይቆ ክስ በቀረበበት ጊዜ ተፈጻሚ እየሆነ ያለዉ በአዋጅ ቁጥር 1243/2013 ጸድቆ ተፈጻሚ እየሆነ ያለዉ የኢፌዲሪ የንግድ ሕግ በመሆኑ ለክርክሩ ተፈጻሚነት ያለዉ ሕግ ማኅበሩ እንዲፈርስ በተጠየቀበት ጊዜ ተፈጻሚ እየሆነ ያለዉ ኋለኛዉ የንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 (ከዚህ በኋላ *የንግድ ሕግ/ጉ* ተብሎ የሚገለጸዉ) እንደሆነ የንግድ ሕጉ ቀዳሚ ጠቅላላ ክፍል ቁጥር 2 እና 7 ያስገነዝባል፡፡

ይህ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር በባህሪዉ በቁጥር ብዛት አነስተኛ በሆኑ ባለአክሲዮኖች የሚቋቋም ሆኖ ማኅበረተኞቹም ዝምድና፣ ቤተሰባዊ፣ የሙያ ወይም የጓደኝነት ግንኙነት ወይም በቅርበት በሚተዋወቁ ሰዎች አማካኝነት በሚሰበሰብ ካፒታል የሚመሰረት ማኅበር በመሆኑ ወይም ለሕዝብ ክፍት በተደረገ የአክሲዮን ሽያጭ የሚቋቋም ባለመሆኑ በኩባንያ ሕግ ዘርፍ ዝግ የንግድ ማኅበር (close corporation)

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በመባል የሚታወቅ ነዉ፡፡ከዚህ ባህሪይዉ የተነሳ በንግድ ሕግ አንቀጽ 495 እና 496 ስር እንደተመለከተዉ ይህ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር የሚቋቋመዉ - ዋና ገንዘቡ በሙሉ አስቀድሞ ሲከፈል እንደሆነ፣ በአክሲዮን የተከፋፈለ እንደሚሆን እና ባለአክሲዮኖች መዋጮአቸዉን ገቢ እስካደረጉ ድረስ ለማኅበሩ ዕዳ ኃላፊ የማይሆኑበት የንግድ ማኅበር እንደሆነ፤የማኅበሩን አክሲዮኖች ለሕዝብ ክፍት በሆነ ገበያ መሸጥ የማይቻልበት እና የማኅበሩ ባለአክሲዮኖች ቁጥር ከሁለት በማያንስና ከሃምሳ ሰዎች ሳይበልጥ ቢያንስ በሕግ የተወሰነ አነስተኛ ዋና ገንዘብ (Capital) ይዞ የሚቋቋም የንግድ ማኅበር ነዉ፡፡ይህንኑ ልዩ ባህሪይዉን ባገናዘበ መልኩ እንዲህ አይነት የንግድ ማኅበር የሚመሰረትበት፣የሚገዛበት፣የሚፈርስበት እና ሒሳብ ተጣርቶ ማኅበሩ ከንግድ መዝገብ የሚሠረዝበትን አግባብ የሚመለከት የሕግ ማዕቀፍ በንግድ ሕጉ ተደንግጎ ይገኛል፡፡

ከላይ በተገለጸዉ መሰረት በሕግ አግባብ የተቋቋመ ኃላፊነቱ የተወሰነ የሕግ ማኅበር በሕግ በተደነገገዉ መሠረት ወይም በፍርድ ቤት በሚሰጥ ውሳኔ ወይም በማኅበርተኞቹ ስምምነት ሊፈርስ ይችላል፡፡ በንግድ ሕጉ ከአንቀጽ 531 እስከ 533 እንዲሁም በአንቀጽ 181 እና 182 ስር ኃላፊነቱ የተወሰነ የንግድ ማኅበር የሚያስፈርሱ ምክንያቶች ፣ ሒሳብ የሚጣራበት እና የፈረሰዉ ማኅበር ከንግድ መዝገብ የሚሠረዝበት አግባብ በዝርዝር ተደንግጓል፡፡በእነዚህ ድንጋጌዎች መሠረት ማኅበሩ የተቋቋመበትን ዓላማ ሲፈጽም ወይም ለመፈጸም ሳይችል ሲቀር፤የማኅበሩ አባላት የማኅበሩ ህልዉና እንዲቀጥል ካልተስማሙ በስተቀር የማኅበሩ የቆይታ ጊዜ ሲጠናቀቅ፤ማኅበርተኞቹ የንግድ ማኅበሩ እንዲፈርስ ሲስማሙ፤የማኅበሩ መክሰር በፍርድ ቤት ሲወሰን፤ በማኅበሩ አባላት መካከል ተቃራኒ ስምምነት ቢኖርም እንኳን በማኅበሩ አባላት መካከል ብርቱ አለመግባባት ኖሮ አለመግባባቱ የማኅበሩ ዓላማ ከግብ እንዳይደርስ በማድረግ ማስተጓጎሉን (በሕጉ የእንግሊዝኛ ቅጅ… if there is a serious disagreement between members and the disagreement obstructs the attainment of the purpose of the organization.) መሠረት በማድረግ በማኅበሩ አባላት ለፍርድ ቤት ጥያቄ ቀርቦ ፍርድ ቤቱም ይህንኑ በማስረጃ አረጋግጦ ማኅበሩ እንዲፈርስ ሲወስን፤ ማኅበሩ አስፈላጊ የሆነ የአስተዳደር አካል የሌለዉ እንደሆነ በባለአክሲዮን ወይም በገንዘብ ጠያቂ ሲጠየቅና ይኸዉ ተረጋግጦ ሥልጣን ባለዉ ፍርድ ቤት ማኅበሩ እንዲፈርስ ሲወሰን፤ የማኅበሩ ዋና ገንዘብ በሦስት አራተኛ በመጉደሉ የዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም ቦርድ የሌለዉ ማኅበር ከሆነ ሥራ አስኪያጁ ማኅበሩ እንዲፈርስ የሚያቀርቡትን ጥያቄ ተቀብለዉ ባለአክሲዮኖቹ ማኅበሩ እንዲፈርስ ሲወስኑ ወይም ሦስት አራተኛ መጠን ያለዉ የማኅበሩ ዋና ገንዘብ መጉደሉ ከታወቀበት ጊዜ አንስቶ በዘጠና ተከታታይ ቀናት ዉስጥ ማኅበረተኞቹ መተካት ካልቻሉ ጥቅም ያለዉ ሰዉ ማኅበሩ እንዲፈርስ ለፍርድ ቤት ሲያመለክትና ፍርድ ቤቱ ማኅበሩ እንዲፈርስ ሲወስን ነዉ፡፡(የንግድ ሕጉ አንቀጽ 181 ፣531 እና 532 ይመለከቷል፡፡)

በሌላ በኩል በንግድ ሕጉ አንቀጽ 181/6 መሰረት በማኅበሩ አባላት መካከል ተቃራኒ ስምምነት ቢኖርም እንኳን በማኅበሩ አባላት መካከል ብርቱ አለመግባባት ኖሮ አለመግባባቱ የማኅበሩ ዓላማ ከግብ እንዳይደርስ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በማድረግ ማስተጓጎሉን መሠረት በማድረግ ማኀበሩ እንዲፈርስ በማኀበሩ አባላት ለፍርድ ቤት ጥያቄ ቢቀርብም እንኳን በዚሁ ሕግ አንቀጽ 181/7 ስር በተደነገገዉ መሠረት የተወሰኑ የማኀበሩ አባላት ድርሻቸዉን ይዘዉ ከማኀበሩ እንዲወጡ በማድረግ በቀሪ አባላት ማኀበሩ ዓላማዉን ለማሳካት በሚችልበት ሁኔታ ማስቀጠል የሚቻል በሆነ ጊዜ አለመግባባቱ ማኀበሩን ለማስፈረስ እንደ በቂ ምክንያት ተደርጎ አይወሰድም፡፡

በሕጉ አንቀጽ 181/6 ላይ "ብርቱ አለመግባባት" በሚል የተገለጸዉ ሀረግ በኩባንያ ሕግ ጽንሰ ሀሳብ በእንግሊዝኛዉ deadlock በመባል የሚታወቅ ሲሆን በሕጉ በእንግሊዝኛ ቅጅ ላይ ደግሞ serious disagreement በሚል የተገለጸ ነዉ፡፡በታዋቂዉ ብላክስ የሕግ መዝገበ ቃል ላይ "deadlock" የሚለዉ ቃል - "The blocking of corporate action by one or more factions of shareholders or directors who disagree about a significant aspect of corporate policy.(Black's Law Dictionary 8th Edition ገጽ 426) የሚል ትርጓሜ የተሰጠዉ ሲሆን ይህም በግርድፉ አንድን ኩባንያ ከሚመለከት መሠረታዊ ፖሊሲ ጋር በተያያዘ በኩባንያ የሚወሰደዉ እርምጃ ተግባራዊ እንዳይሆን አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ የባለአክሲዮኖች ወይም የዳይሬክተሮች ቡድን በመቃወም እርምጃ እንዳይወሰድ ሲገድቡ ነዉ፡፡" የሚል ትርጓሜ ያለዉ ነዉ፡፡

ሌሎች በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ትንተና በመጻፍ የሚታወቁት የሕግ ባለሙያዎች በአንድ በታተመ ጽሑፋቸዉ ላይ - Deadlock is defined as "a decision or indecision of stockholders, which results in the corporation's inability to perform its corporate powers… . Deadlocks can be related to several types of decision-making failure, particularly: "1) The failure of equal members or managers to reach agreement; 2). The failure to obtain a required majority vote; 3). The failure to obtain a required approval from a member with approval rights; and 4). The failure to obtain unanimous consent where unanimity is required.'' (Louis T. M. Conti, Lisa R. Jacobs, Steven N. Leitess,Deadlock-Breaking Mechanisms in LLCs—Flipping a Coin Is Not Good Enough, but Is Better Than Dissolution.'' Business Law Today, March 23, 2017; https://www.americanbar.org/groups/ business_law/ publications/blt/2017/03/03 _conti/ Last Seen: 05.09.2021)) በማለት ገልጸዉታል፡፡ ሌላዉ ጸሐፊ በተመሳሳይ The clearest example of a deadlock occurs where there is at once a dispute between two 50 percent shareholders and between two numerically equal factions comprising the board of directors. ( Field, Harold D. Jr., "Resolving Shareholder Disputes and Breaking Deadlocks in the Close Corporation" (1974), Minnesota Law Review. 1427. https://scholarship.law.umn.edu/mlr/1427) በማለት ገልጸዉታል፡፡ ይህም - " ብርቱ አለመግባባት ማለት ኩባንያዉ ድርጅታዊ ሥልጣኑን መጠቀም እንዳይችል የሚያደርግ ዉጤት በሚያስከትል አኳኋን በባለአክሲዮኖች መወሰን ወይም አለመወሰን ነዉ፡፡ ብርቱ አለመግባባት በብዙ መልኩ የሚገለጽ ዉሳኔ መስጠት አለመቻል ሲሆን በተለይም - 1) እኩል ቁጥር ያላቸዉ አባላት ወይም ሥራ አስኪያጆች ስምምነት ላይ መድረስ አለመቻል፤2)አስፈላጊ የሆነዉን አብላጫ ድምጽ ማግኘት አለመቻል፤ አንድን ዉሳኔ ለማስተላለፍ ወሳኝ ድምጽ ካላቸዉ አባላት የይሁንታ ድምጽ

ማጣት እና 4) በተባበረ ድምጽ ዉሳኔ በሚጠይቅ ጉዳይ ላይ በተባበረ ድምጽ ዉሳኔ መስጠት አለመቻል። ብርቱ አለመግባባትን በግልጽ ምሳሌ ለማስረዳት - ብርቱ አለመግባባት በተመሳሳይ ሰዓት ሁለት 50 ከመቶ የአክሲዮን ድርሻ ያላቸዉ ባለአክሲዮኖች እና በዳይሬክተሮች ቦርድ ዉስጥ እኩል ቁጥር ያላቸዉ ዳይሬክተሮች መካከል ክፍፍል በመፈጠሩ ዉሳኔ ማሳለፍ አለመቻል ነዉ።"በሚል የገለጹበት ነዉ።

በአገራችን የኩባንያ ሕግ ላይ መጽሐፍ የጻፉት የሕግ ምሁር ፈቃዱ ጴጥሮስ ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘ በመጽሐፋቸዉ የሚከተለዉን ሀሳብ አስፍረዋል፦

ብርቱ አለመግባባት የሚለዉ ሐረግ በሌሎች አገራት ሕግ ብዙዉን ጊዜ deadlock የሚለዉን ይወክላል። deadlock ተፈጥሯል የሚባለዉ የኩባንያዉን የሥራ እንቅስቃሴ ለማስቀጠል እንቅፋት የሚሆን የ50፡50 ድምጽ አንድን ዉሳኔ በሚደግፉት እና በሚቃወሙት መካከል ሲፈጠር ነዉ። …ኩባንያዉ በዚህ አይነት ሁኔታ ዉስጥ ከገባ እንዲፈርስ ከአባላት አንዱ ለፍርድ ቤት ጥያቄ ማቅረብ ይችላል።…በአባላት መካከል የማኅበሩን የንግድ እንቅስቃሴ በሚመለከት የቱንም ያህል ብርቱ ጭቅጭቅና ያለመግባባት ቢፈጠር በድምጽ ብልጫ ዉሳኔዎች ማለፍ እስከቻሉ ድረስ ለማፍረስ የሚያደርስ ምክንያት አይሆንም።የእኛ አገር ፍርድ ቤቶችም ይህን ብርቱ ጭቅጭቅ የሚለዉን ሀሳብ ብዙዉን ጊዜ ከላይ ያየነዉን deadlock የሚለዉን ሀሳብ ባዘለ መልኩ ነዉ የሚተረጉሙት።ምክንያም በአብዛኞቹ የፍርድ ቤቶቻችን ዉሳኔዎች መሠረት ብርቱ ጭቅጭቅ ከኩባንያዉ የንግድ ሥራ ጋር የተያያዘ መሆነ አለበት ስለሚሉ ነዉ።…እዚህ ላይ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ግላዊ ማንነት ላይ የተመሠረተ መሆኑ መዘንጋት የለበትም።ግላዊ ግንኙነት አደጋ ላይ ከወደቀ ደግሞ ማኅበሩ ሊቀጥል አይችልም።ፍርድ ቤቶች ብርቱ ጭቅጭቅ የሚለዉን አጥብበዉ የሚተረጉሙት የኩባንያዎች መፍረስ በዜጎች የሥራ እድል ላይ እንዲሁም በአገር ኢኮኖሚ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያመጣል በሚል እንደሆነ ከዉሳኔዎቻቸዉ መመልከት ይቻላል።ነገር ግን ሁል ጊዜ የኩባንያ መፍረስ የንግድ ድርጅቱን መፍረስ ላያስከትል ይችላል።…ኩባንያ እንዳይፈርስ ጥረት ማድረግ ተገቢ ቢሆንም አብረዉ በማኅበር መቀጠል የሌለባቸዉን ሰዎች አስገድዶ አንድ ላይ እንዲሰሩ በማድረግ ሊሳካ አይችልም። (ፈቃዱ ጴጥሮስ ገ/መስቀል፣(ሦስተኛ የተሻሻለ እትም)፣የኢትዮጵያ የኩባንያ ሕግ፡አዲሱ የንግድ ሕግ የተካተተበት፣(2014) ገጽ 443-445 ይመለከቷል።)

ይህ ሰበር ችሎት ከዚህ ቀደም በሰ/መ/ቁጥር 143390፣157305፣153981 እና 234731 ላይ በሰጠዉ ዉሳኔ አንድን የንግድ ማኅበር ሊያስፈርስ የሚችል ብርቱ ጭቅጭቅ (በአዲሱ የንግድ ሕግ ብርቱ አለመግባባትን በሚል የተገለጸ መሆኑ ልብ ይሏል) ተፈጥሯል የሚስብሉ ሁኔታዎች ምንነት በተመለከተ የቀድሞዉን የንግድ ሕግ አንቀጽ 218 መሰረት በማድረግ የሰጠዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ከፍ ሲል የተጠቀሱት የሕግ ምሁር በመጽሐፋቸዉ ከገለጹት ጋር ተመሳሳይነት ያለዉ ነዉ።

በተያዘዉ ጉዳይ ግራ ቀኙ አባል የሆኑበት ማኅበር እንዲፈረስ በስር ፍርድ ቤቶች የተወሰነዉ "…በማኅበረተኞቹ መካከል በተፈጠረ አለመግባባት የተነሳ ማኅበሩ መደበኛ ሥራውን በመሥራት ላይ የማይገኝ መሆኑ በሰው ምስክር እና በሰነድ ማስረጃ በመረጋገጡ፤ በዚህም ምክንያት በአሁኑ ጊዜ ማኅበሩ መክሰሩን ግራ ቀኙ ያልተካካዱ በመሆኑ፤በዚህ ሁኔታ ማኅበሩ የተቋቋመበትን ዓላማ ያሳካል ተብሎ ስለማይገመት ማኅበሩ ሊፈርስ ይገባል፡፡" በሚል ነዉ፡፡ በዚህ መልኩ ከተጠቀሱት ምክንያቶች ዉስጥ አንዱ ማኅበሩ መክሠሩን ግራ ቀኙ አልተካካዱም የሚል ቢሆንም በንግድ ሕጉ አንቀጽ 705 እና ተከታዮቹ ድንጋገዎች መሠረት ማኅበሩ መክሰሩ በፍርድ እንዲወሰን የመክሠር ሥነ ሥርዓት ተከፍቶ በሕግ በተዘረጋዉ ሥርዓት መሠረት ማኅበሩ ከሥሯል በሚል የተላለፈ ፍርድ የሌለ ስለመሆኑ የግራ ቀኙ ክርክር ያሳያል፡፡ የስር ፍርድ ቤቶችም በዚህ አግባብ የተሰጠ የመክሠር ፍርድ እንዳለ በፍርዳቸዉ አልገለጹም፡፡ በተጨማሪም ማኅበሩ እንዲፈርስ ክስ የመሠረቱት ተጠሪዎች ማኅበሩ እንዲፈርስ ባቀረቡት የክስ አቤቱታ ላይ ማኅበሩ በመክሰሩ ይሄዉ ተረጋግጦ ማኅበሩ እንዲፈርስ እንዲወሰን የማኅበር መክሠር የክስ ምክንያት በማድረግ የጠየቁት ዳኝነት ካለመኖሩም በተጨማሪ በንግድ ሕግ አንቀጽ 600/1 እና 706(1/ሀ) ስር በተደነገገዉ መሠረት የንግድ ማኅበር መክሠርን እንዲያዉጅ ሥልጣን የተሰጠዉ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሆኑ የስር የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን የለዉም፡፡በመሆኑም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማኅበሩ ከስሯል የሚል ምክንያት ለማኅበሩ መፍረስ ምክንያት ማደረጉ ከንግድ ሕጉም ሆነ ከክርክር አመራር አኳያ ሊታረም የሚገባዉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ ብለናል፡፡

ከላይ እንደተገለጸዉ የንግድ ማኅበር አባላት ካላቸዉ ሕጋዊ መብቶች መካከል አንዱ በሕግ የማኅበር ማስፈረሻ ምክንያት እንደሆነ እዉቅና የተሰጠዉ ሁኔታ መኖሩን በማረጋገጥ ማኅበሩ እንዲፈርስ ለመጠየቅ ያላቸዉ መብት ነዉ፡፡ማኅበረተኞቹ በተለይም በመካከላቸዉ የተፈጠረዉን አለመግባባት ምክንያት በማድረግ የንግድ ማኅበሩ እንዲፍርስ ለመጠየቅ መብት ቢኖራቸውም ፍርድ ቤቱ የንግድ ማኅበሩ እንዲፈርስ ውሳኔ የሚሰጠው ማኅበሩ እንዲፈርስ ስለተጠየቀ ብቻ ሳይሆን የንግድ ማኅበሩን ሊያስፈርስ የሚችል በሕግ እዉቅና የተሰጠዉና ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ በቂ ምክንያት መኖሩን ያረጋገጠ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ በዚህ ልክ የንግድ ማኅበር የሚያስፈርስ ምክንያት መኖሩ ሳይረጋገጥ የንግድ ማኅበር እንዲፈርስ ውሳኔ የሚሰጥ ከሆነ ማኅበርተኞቹ ማኅበሩን ያቋቋሙበት ዓላማ ሳይሳካ ያለበቂ ምክንያት ማኅበሩ ህልዉናዉን እንዲያጣ ከማድረግም አልፎ አገሪቱና ኅብረተሰቡ በጠቅላለዉ ከንግድ ማኅበራት ማግኘት የሚችሉትን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጥቅሞችን እንዲያጡ የሚያደርግ አሉታዊ ዉጤት የሚያስከትል በመሆኑ ተቀባይነት ሊኖረዉ አይገባም፡፡ ይህ የማይፈለግ አሉታዊ ዉጤት እንዳይከሰት ከላይ ከተጠቀሱት የሕጉ ድንጋጌዎች አቀራረጽ፣ ይዘት፣ መንፈስና ዓላማ መገንዘብ እንደሚቻለዉ የንግድ ማኅበራት በቂና አሳማኝ ባልሆነ ምክንያት እንዳይፈርሱ ብርቱ ጥንቃቄ በማድረግ በሕጉ ተለይተዉ በተደነገጉት ምክንያቶች ብቻ የምክንያቶቹ ትክክለኛነትና በቂነት በተገቢዉ ማስረጃ ተረጋግጦ በመርህ ደረጃ የማኅበሩን ህልዉና ለሚያስቀጥሉ የመፍትሄ እርምጃዎች ቅድሚያ በመስጠትና አሟጦ ተግባራዊ ማድረግ ይገባል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በአንጻሩ በማኅበሩ አባላት መካከል የተፈጠረ ብርቱ አለመግባባት መኖሩ ተረጋግጦ በዚህ የተነሳ የተወሰኑ የማኅበሩ አባላት ድርሻቸዉን ይዘዉ ከማኅበሩ እንዲወጡ በማድረግ በቀሪ አባላት ማኅበሩ ዓላማዉን ለማሳካት በሚችልበት ሁኔታ ማስቀጠል እንደማይቻል ሲረጋገጥ ማኅበር የማፍረስ መፍትሄ የመጨረሻ አማራጭ እርምጃ አድርጎ በጠባቡ ተግባራዊ ማድረግ ይገባል፡፡

ከላይ በዝርዝር የተገለጸዉን ከግምት በማስገባት የስር ፍርድ ቤቶች ግራ ቀኙ አባል የሆኑበት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር እንዲፈርስ የወሰኑት በሕጉ እና ተቀባይነት አግኝቶ በአገራችን ዳኝነታዊ ፍልስፍና (judicial jurisprudence) በዳበረዉ መሠረት በማኅበሩ አባላት መካከል ማኅበሩን ለማስፈረስ የሚችል በቂና ትክክለኛ ምክንያቶች የተደገፈ ብርቱ አለመግባባት መኖሩን አረጋግጠዉ ነዉ ወይ? የሚለውን በንግድ ሕጉ አንቀጽ 181(6 እና 7) ስር ከተደነገጉት መመዘኛዎች አንጻር እንደሚከተለዉ ተመልክተናል፡፡

የስር ከሳሾች በአባላት መካከል ያለው አለመግባባት በጋራ ለመሥራት በማያስችል ደረጃ ላይ ስለደረሰ ማኅበሩ እንዲፈርስ ይወስንልን በማለት የጠየቁት ዳኝነት የክስ ምክንያት አድርገዉ የገለጿቸዉን ምክንያቾች በቂነትና አግባብነት በንግድ ሕጉ አንቀጽ 181/6 ስር *"…የማኅበሩ ዓላማ ከግብ እንዳይደርስ የሚያስተጓጉል ሲሆን"* በሚል ከተደነገገዉ መስፈረት አንጻር ከመመርመራችን በፊት በማኅበሩ አባላት መካከል *"ብርቱ አለመግባባት/deadlock"* አለ በሚል በስር ፍርድ ቤቶች በተደረሰበት ድምዳሜ ላይ የተፈጸመ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡ ከላይ እንደተመለከትነዉ ብርቱ አለመግባባት ተፈጥሯል የሚባለዉ ማኅበሩ የተቋቋመበትን የሥራ እንቅስቃሴ ለማስቀጠል እንቅፋት በሚሆን ደረጃ አንድን የማህበሩን ዉሳኔ በሚደግፉት እና በሚቃወሙት አባላት መካከል የ50:50(እኩል የሆነ የሃምሳ ሃምሳ) ድምጽ ሲፈጠር ወይም ደግሞ እኩል ቁጥር ባላቸዉ አባላት መካከል የማኅበሩን የሥራ እንቅስቃሴ ለማስቀጠል አስፈላጊ በሆነ ስምምነት ላይ ለመድረስ አስፈላጊ የሆነዉን አብላጫ ድምጽ ማግኘት ሳይቻል ሲቀር ብርቱ አለመግባባት ተፈጥሯል ሊባል እንደሚችል ነዉ፡፡ ሆኖም የስር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ከዚህ አኳያ አለመመርመራቸዉን ተረድተናል፡፡ በቀን 20/05/2000ዓ/ም በተመዘገበዉ በተሻሻለዉ የማኅበሩ መመስረቻ ጽሁፍ ላይ የማኅበሩ አክሲዮን ብዛት የእያንዳንዱ ዋጋ ብር 1000.00 የሆኑ 15,988 አክሲዮኖች እንድሆኑ፤ ተጠሪዎች በ2006 ዓ/ም የአባላትን የአክሲዮን በእጥፍ ለማሳደግ በተደረገዉ ጠቅላላ ጉባኤ በመወሰኑ ጠቅላላ የአክሲዮን ብዛት 31,976 ሆኗል በማለት የገለጹትን አመልካቾች በጠበቃቸዉ አማካኝነት ለዚህ ችሎት በቀን 14/06/ 2017ዓ/ም በቃል ባሰሙት ክርክር በ2006ዓ/ም በተደረገ ጠቅላላ ጉባኤ ስላልተሳተፍን የአክሲዮን ብዛት በእጥፍ እንዲያድግ መወሰኑን አናዉቅም በማለት የተከራከሩ ቢሆንም ይህንን ቃለ ጉባዔ እንዳላስፈረሱ ለችሎቱ አስረድተዋል፡፡እንዲሁም የማኅበሩ አባል የነበሩትን ዘላለም መኮንን አባተን ወራሽ ለመተካት በቀን 03/10/2011 ዓ/ም በተደረገ እና በፌዴራል ሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ በተመዘገበ ቃለ ጉባኤ ላይ የማኅበሩ አጠቃላይ አክሲዮን ብዛት 31,976 እንደሆነ ስለሚያሳይና ቃለ ጉባዔዎቹ ጸንተዉ ስለሚገኙ የማኅበሩ ጠቅላላ አክሲዮን ብዛት 31,976 እንደሆነ ተገንዝበናል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት በቃል ባሰሙት ክርክር ላይ በተመሳሳይ ከገለጹት መረዳት እንደተቻለዉ የማኅበሩ አባላት ብዛት 25 ሲሆኑ እያንዳንዳቸዉ ያላቸዉ አክሲዮን ብዛት የተለያየ ነዉ፡፡ በስር ፍርድ ቤት ማኅበሩ እንዲፈርስ ዳኝነት በመጠየቅ በአመልካቾች ላይ ክስ የመሠረቱ አባላት ብዛት 14 እንደሆኑ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ይዘት ያሳያል፡፡በቀን 03/10/2011 ዓ/ም በተደረገ ወይም በቀን 08/11/2011 ዓ/ም በተመዘገበ ቃለጉባዔ መሠረት እነዚህ 14 አባላት ያላቸዉ ጠቅላላ የአክሲዮን ድርሻ 20,824 ሲሆን ይህም ከአጠቃላይ አክሲዮን አኳያ በመቶኛ ሲሰላ 65.12 ከመቶ አክሲዮን ያላቸዉ አባላት ያደርጋቸዋል፡፡የተጠቀሰዉ ያህል አክሲዮን ያላቸዉ አባላት ማኅበሩ እንዲፈርስ ክስ መስርተዉ የስር ፍርድ ቤቶች ማኅበሩ እንዲፈርስ ከወሰኑ በኋላ በቀን 19/06/2016 ዓ/ም በተደረገ የእርቅ ስምምነት ማድረጋቸዉን ለችሎቱ ከማሳወቃቸዉም በተጨማሪ ለአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መልስ እንዲሰጡ ይህ ችሎት ትእዛዝ ከሰጠ በኋላ በቀን 25/11/2016 ዓ/ም በሰጡት መልስ የአሁን 1ኛ፣2ኛ፣ 9ኛ እና 10ኛ ተጠሪዎች ማኅበሩ ሊፈርስ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡የ1ኛ፣2ኛ፣9ኛ እና 10ኛ ተጠሪዎች አጠቃላይ አክሲዮን ብዛት 7,672 ይሆናል፡፡ይህም ማኅበሩ ሊፈርስ ይገባል በማለት ከሚከራከሩት 14 አባላት አክሲዮን ብዛት ከሆነዉ ከ20,824 አክሲዮን ላይ ሲቀነስ ማኅበሩ ሊፈርስ ይገባል በማለት ክስ የመሰረቱ ተጠሪዎች ጠቅላላ አክሲዮን ብዛት 13,152 ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል በስር ፍርድ ቤት ከሳሽ ከነበሩት ዉስጥ ሎዛ ጌድዮን እና ራኬብ ጌድዮን የተባሉ አባላት በዚህ ችሎት በተደረገ ክርክር ተጠሪ ያልተደረጉ ቢሆንም በዚህ ሰበር ችሎት ክርክር እየተደረገ መሆኑን የ4ኛ፣ 5ኛ፣6ኛ፣7ኛ፣8ኛ፣11ኛ እና 12ኛ ተጠሪዎች ጠበቃ ከእነርሱ ዉክልና ስላለኝ ማኅበሩ ሊፈርስ ይገባል ከሚሉት ወገን ናቸዉ በማለት ቢገልጹም የእነርሱም ጠበቃ ከሆኑ በክርክሩ ተካፋይ ሳይሆኑ የሚሰጠዉ ዉሳኔ መብታቸዉን ሊነካ ይችላል በሚል በክርክሩ ተካፋይ እንዲሆኑ ማድረግ እየቻሉ ይህንን ያላደረጉ በመሆኑ እነርሱም በክርክሩ ተካፋይ መሆን አለብን በማለት መጠየቅ እየቻሉ ይህንን ያላደረጉ በመሆኑ የተጠቃሾቹ አባላት ጠቅላላ አክሲዮን የሆነዉ 1,096 ማኅበሩ ሊፈርስ ይገባል ከሚሉት ወገን ናቸዉ ብሎ ለመደምደም የሚያስችል ምክንያት ችሎቱ አላገኘም፡፡ እንዲሁም በስር ፍርድ ቤት ማኅበሩ እንዲፈርስ ክስ የመሰረቱት የአሁን 3ኛ ተጠሪ 2192 አክሲዮን ያላቸዉ ሲሆን በዚህ ችሎት ቀርበዉ እንዲከራከሩ መጥሪያ ተልኮላቸዉ ቀርበዉ ባለመከራከራቸዉ አሁንም ማኅበሩ ይፍረስ የሚል አቋም አላቸዉ ብሎ ለመደምደም አልተቻለም፡፡ በመሆኑም የእነዚህ የሦስቱ አባላት አክሲዮን ማኅበሩ ሊፈርስ ይገባል በማለት ክስ ከመሰረቱት አባላት ጠቅላላ አክሲዮን ካላቸዉ 13,152 አባላት መካከል ማኅበሩ ሊፈርስ ይገባል በማለት በዚህ ችሎት ጭምር አጥብቀዉ የሚከራከሩት አባላት የአሁን 4ኛ፣5ኛ፣6ኛ፣7ኛ፣8ኛ፣11ኛ እና 12ኛ ተጠሪዎች ሲሆኑ የእነርሱ ጠቅላላ የአክሲዮን ብዛት ደግሞ 9864 ይሆናል፡፡ ይህም ከአጠቃላይ 31,976 አክሲዮን ጋር ሲነጻጸር ማኅበሩ ይፍረስ በማለት የሚከራከሩ ተጠሪዎች የአክሲዮን ብዛት በመቶኛ 30.8 ከመቶ ሲሆን ማኅበሩ ሊፈርስ አይገባም በማለት የተከራከሩ አባላት፣በዕርቅ ስምምነት ማኅበሩ ሊፈርስ አይገባም በማለት የዕርቅ ስምምነት የፈጸሙ አባላት፣ በስር ፍርድ ቤት ከሳሽ የነበሩ በዚህ ችሎት በተጠሪነት ቀርበዉ

ያልተከራከሩ እንዲሁም በስር ፍርድ ቤት ተከራካሪ ባለመደረጋቸዉ ምክንያት ወይም በሞት በመለየታቸዉ ምክንያት ማኅበሩ ይፍረስ ወይም ሊፈርስ አይገባም በማለት በግልጽ ሀሳባቸዉን ያልገለጹ አባላትን እና በስር ፍርድ ቤት ማህበሩ ሊፈርስ ይገባል በማለት ተከራክረዉ በዚህ ችሎት መጥሪያ ደርሷቸዉ ቀርበዉ ማህበሩ ሊፈርስ ይገባል በማለት ያልተከራከሩትን 3ኛ ተጠሪን ጨምሮ ቀሪዉ የአክሲዮን ብዛት 69.2 ከመቶ እንደሆነ ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት ካሰሙት ክርክር ተገንዝበናል፡፡

ከላይ በተገለጸዉ መሠረት ብርቱ አለመግባባት በመካከላቸዉ እንደተፈጠረ በመግለጽ ከስር ፍርድ ቤት ጀምሮ በዚህ ችሎት ጭምር ማኅበሩ እንዲፈርስ አጥብቀዉ የተከራከሩ አባላት ያላቸዉ አጠቃላይ የአክሲዮን ብዛት 9,864 ወይም 30.8 ከመቶ ሲሆን ቀሪዉ አክሲዮን ደግሞ በመቶኛ 69.2 ከመቶ ነዉ፡፡በተያዘዉ ጉዳይ ግራ ቀኙ በደፈናዉ ብርቱ አለመግባባት ተፈጥሯል፤ አልተፈጠረም በሚል ከመከራከር ባለፈ ከላይ በተገለጸዉ መሠረት የማኅበሩን ዉሳኔ በሚደግፉት እና በሚቃወሙት አባላት መካከል የ50፡50 ድምጽ ክፍፍል መኖሩን በመግለጽ ወይም በማኅበሩ አባላት መካከል የተፈጠረዉ ክፍፍል የማኅበሩን ሥራ እንቅስቃሴ ለማስቀጠል አስፈላጊ በሆነ ጉዳይ ላይ በአብላጫ ድምጽ ዉሳኔ መስጠት እንዳይቻል አድርጎናል በማለት በግልጽ ካለመከራከራቸዉም በተጨማሪ የድምጽ ክፍፍሉ ሲታይም ማኅበሩ የተቋቋመበትን የሥራ እንቅስቃሴ ለማስቀጠል እንቅፋት የሚሆን አይደለም፡፡ በሌላ አነጋገር ማኅበሩ ሊፈርስ ይገባል በማለት የሚከራከሩ አባላት ያላቸዉ ድምጽ 50 ከመቶ በታች በመሆኑ በቀሪዎቹ አባላት የማኅበሩን የሥራ እንቅስቃሴ ወይም ህልዉና ማስቀጠል እንደሚቻል ተገንዝበናል፡፡ እንዲሁም የአሁን 4ኛ፣5ኛ፣6ኛ፣7ኛ፣ 8ኛ፣11ኛ እና 12ኛ ተጠሪዎች ጠበቃ በተሻሻለዉ የማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 7 መሠረት በማኅበሩ ስብሰባዎች ላይ ዉሳኔ የሚተላለፈዉ 75 ከመቶ ባለአክሲዮኖች ድጋፍ ሲኖር ስለሆነ ማኅበሩ አይፍረስ የሚሉ አባላት 75 ከመቶ ድርሻ ያላቸዉ ስላልሆኑ ማኅበሩ ሊፈረስ ይገባል በማለት የተከራከሩ ቢሆንም እንዲህ አይነት ክርክር በስር ፍርድ ቤት በግልጽ አንስተዉ ባለመከራከራቸዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 329/1 መሰረት በዚህ ረገድ የቀረበዉን ክርክር አልተቀበልንም፡፡በመሆኑም በንግድ ሕጉ አንቀጽ 181/6 ስር በተደነገገዉ መሠረት የማኅበሩን የሥራ እንቅስቃሴ ለማስቀጠል እንቅፋት የሚሆን ብርቱ አለመግባባት (*deadlock*) በማህበሩ አባላት መካከል አልተፈጠረም ብለናል፡፡

በተጨማሪም በስር ፍርድ ቤቶች ማኅበሩ እንዲፈርስ የተወሰነዉ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 181/6 ስር *"…የማኅበሩ ዓላማ ከግብ እንዳይደርስ የሚያስተጓጉል ሲሆን"* በሚል የተደነገገዉ ተጨማሪ መስፈርት መሟላቱን አረጋግጠዉ ነዉ ወይ? የሚለዉን ስንመረምር የስር ከሳሾች ማኅበሩ እንዲፈርስ ዳኝነት በጠየቁበት ክስ ላይ የክስ ምክንያት አድርገዉ የጠቀሷቸዉ ምክንያቶች - የአሁን አመልካቾች(የስር ተከሳሾች) 1) አባታችን ተክተን የቦርድ አባል ካልሆንን በማለት በተለያየ ጊዜ ሁከት እና ረብሻ ፈጥረዋል፣2) እንደማንኛውም አባል ከማኅበሩ እኩል መብት እያላቸው በሕገ-ወጥ መንገድ በተለያየ ጊዜ ስብሰባ እንዲደረግ ማድረጋቸው፣ 3) በሚደረግ ስብሰባ ላይ ሁከት ማንሳትና የቦርድ አባላት ሥራቸውን በአግባቡ

እንዳያከናውኑ ሥራ ቦታ ሄደው ሁከት በመፍጠር በየእለቱ በሚከናወን የማኅበሩ ሥራ ጣልቃ መግባት 4) ጠቅላላ ጉባዔ ይጠራ በሚል ምክንያት የማኅበሩን ሂሳብ እንዳይንቀሳቀስ በፍርድ ቤት ማሳገድ፤ እና የቦርድ አባል በሆኑት 7ኛ ተጠሪ ላይ የወንጀል ክስ በፍርድ ቤት መስርተዋል፤ 5) በአባላት መካከል መልካም ግንኙነት እንዳይኖር እና በጋራ መሥራት እንዳይቻል ማድረግና በዚህም ምክንያት ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ መልካም ግንኙነት እና መረዳዳት ስለሌለ ማኅበሩ የተቋቋመበትን ዓላማ ከማሳካት ኪሳራ ውስጥ እንዲገባ ማድረግ የሚሉ ናቸዉ።እነዚህ ምክንያቶች በአመልካቾች ተፈጥረዋል ወይስ አልተፈጠሩም የሚለዉን ማረጋገጥ የሚገባ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ምክንያቶቹ ጠቅለል ተደርገዉ ሲታዩ በአንድ በኩል አመልካቾች የማኅበሩ አባል በመሆናቸዉ ሊከበርልን ይገባል የሚሉትን መብትና ጥቅም ለማስከበር የፈጸሙት እንደሆነ የሚቆጠሩ ሲሆኑ በሌላ በኩል ደግሞ ከሕግ አግባብ ዉጭ ማኅበሩ የተቋቋመመበትን ዓላማ እንዳይፈጽም በሚያደርግ አኳኋን አመልካቾች(የስር ተከሳሾች) ሁከት እና ረብሻ ፈጽመዉ ከሆነ ማኅበሩ በራሱ የሕግ ሰዉነት ያለዉ በመሆኑ ይህንን ድርጊት የፈጸመ አባል አንደማንኛዉም ሰዉ በሕግ አግባብ ተጠያቂ እንዲሆን በማድረግ መብቱን ማስከበር ከሚችል በስተቀር ተጠቃሾቹ ምክንያቶች በንግድ ሕጉ አንቀጽ 181/6 ስር በተደነገገዉ መሠረት *የማኅበሩ ዓላማ ከግብ እንዳይደርስ ሊያስተጓጉሉ* የሚችሉ ምክንያቶች ስላልሆኑ ማኅበሩን ለማስፈረስ የሚያበቁ ምክንያቶች አይደሉም ብለናል።

ከላይ እንደተገለጸዉ በግራ ቀኙ መካከል ተፈጠረ የተባለዉ አለመግባባት ብርቱ አለመግባባት (*deadlock) ተደርጎ ሊወሰድ የማይችል መሆኑ ከተረጋገጠ እና የማኅበሩ ዓላማ ከግብ እንዳይደርስ ሊያስተጓጉሉ* የሚችሉ ምክንያቶች በመካከላቸዉ አልተፈጠረም ካልን ማኅበሩ ሊፈርስ ይገባል እንጂ ተግባብተን ማኅበሩ የተቋቋመበትን ዓላማ እንዲፈጽም ማድረግ አንችልም በማለት አጥብቀዉ የሚከራከሩት የአሁን 4ኛ፣5ኛ፣ 6ኛ፣7ኛ፣ 8ኛ፣11ኛ እና 12ኛ ተጠሪዎች በማኅበሩ የሚኖራቸዉ መብት ምን ሊሆን ይገባል የሚለዉ ነጥብ የዚህን ችሎት ዉሳኔ የሚሻ ሌላዉ ነጥብ ነዉ። ችሎቱ ለዚህ ነጥብ ዉሳኔ ሊሰጥ የሚገባዉ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 181/7 መሰረት እንደሆነ ተገንዝቧል።ይኸዉም " በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 ላይ የተደነገገዉ ቢኖርም የተወሰኑትን የማኅበሩን አባላት ድርሻቸዉን ይዘዉ ከማኅበሩ እንዲወጡ በማድረግ በቀሪ አባላት ማኅበሩ ዓላማዉን ለማሳካት በሚችልበት ሁኔታ ማስቀጠል የሚቻል በሆነ ጊዜ አለመግባባቱ ማኅበሩን ለማስፈረስ እንደ በቂ ምክንያት ተደርጎ አይወሰድም።" በሚል የተደነገገ ነዉ።ከፍ ሲል እንደተገለጸዉ በግራ ቀኙ መካከል የተፈጠረዉ አለመግባባት ብርቱ ካለመሆኑም በተጨማሪ የማኅበሩ ዓላማ ከግብ እንዳይደርስ ሊያስተጓጉል የሚችል አለመሆኑ የተረጋገጠ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 181/6 አነጋገር መሰረት በአባላቱ መካከል የማኅበሩን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የማያስችል ብርቱ አለመግባባት ቢፈጠር እንኳን በቀሪ አባላት ማኅበሩ ዓላማዉን ለማሳካት የሚችልበት ሁኔታ ያለ እንደሆነ የተወሰኑት የማኅበሩ አባላት ድርሻቸዉን ይዘዉ ከማኅበሩ እንዲወጡ ይደረጋል እንጂ ማኅበሩ እንዲፈርስ መወሰን አይቻልም።

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ሲጠቃለል በግራ ቀኙ መካከል ተፈጠረ የተባለዉ አለመግባባት በንግድ ሕጉ አንቀጽ 181(6 እና 7) መንፈስና ዓላማ መሠረት ብርቱ አለመግባባት ሊባል የሚችል ካለመሆኑም በተጨማሪ የማኅበሩ ዓላማ ከግብ እንዳይደርስ በማድረግ ሊያስተጓጉል የሚችል ተግዳሮት አልገጠማቸዉም ብለናል፡፡ስለሆነም ማኅበሩ ሳይፈርስ ከቀሪዎቹ የማኅበሩ አባላት ጋር በመሆን በማኅበር አባልነት መቀጠል ስለማንችል ማኅበሩ ሊፈርስ ይገባል በማለት እስከዚህ ሰበር ችሎት ድረስ አጥብቀዉ የተከራከሩት አባላት ድርሻቸዉን ይዘዉ ከማኅበሩ እንዲወጡ እና የማኅበሩ ህልዉና እንዲቀጥል ወስነናል፡፡ የስር የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከዚህ በላይ በዝርዝር ከተገለጸዉ አንጻር እና የተከሳሽ ከሳሽነት ክሱን ባገናዘበ አኳኋን ጉዳዩን በመመልከት ማኅበሩ ሊፈርስ ይገባል በማለት የተከራከሩ አባላት ክርክር በበቂ ምክንያት የተደገፈ እንዳልሆነ በመግለጽ በማኅበር አባልነት ለመቀጠል ስላልፈለጉ ድርሻቸዉን ይዘዉ ከማኅበሩ እንዲወጡ በማድረግ ማኅበሩ ሊፈርስ አይገባም በማለት መወሰን ሲገባዉ በቂ ባልሆነ ምክንያት ማኅበሩ እንዲፈርስ ዉሳኔ መስጠቱም ሆነ ይህንን ዉሳኔ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተዉ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በማጽናት መወሰኑ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ለ) እና 10(1/ሠ) መሠረት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ብለናል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ዉሳኔ</u>

1. የአዳማ ልዩ ዞን ክፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 42453 ላይ በቀን 25/01/2016 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 434926 ላይ በቀን 18/04/2016 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 መሠረት ተሽረዋል፡፡

2. ናዝሬት እና አርሲ ሳሙና እና ዘይት ፋብሪካ ኃላ/የተ/የግ/ማኅበር ሊፈርስ አይገባም ብለናል፡፡ ስለሆነም 4ኛ፣5ኛ፣ 6ኛ፣7ኛ፣ 8ኛ፣11ኛ እና 12ኛ ተጠሪዎች ከማኅበሩ አባልነት እንዲወጡ እና የማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ ተሻሽሎ በቀሪዎቹ አባላት የማኅበሩ ህልዉና እንዲቀጥል ተወስኗል፡፡ እንዲሁም ጠቅላላ ጉባዔ ተጠርቶ በሚተላለፍ ዉሳኔ መሠረት እነዚህ አባላት ያላቸዉ አክሲዮን ለቀሪ የማኅበሩ አባላት እንዲተላለፍ ተወስኗል፡፡

3. 4ኛ፣5ኛ፣ 6ኛ፣7ኛ፣ 8ኛ፣11ኛ እና 12ኛ ተጠሪዎች በዚህ ዉሳኔ ተራ ቁጥር 2 በተመለከተዉ መሠረት ድርሻቸዉን በአግባቡ ማግኘት ካልቻሉ የማኅበሩ ሂሳብ በኦዲተር ተጣርቶ እያንዳንዳቸዉ ካላቸዉ አክሲዮን ብዛት አንጻር ድርሻቸዉን በማሳየት ድርሻቸዉ እንዲሰጣቸዉ (እንዲከፈላቸዉ) ተገቢዉን ክስ በማቅረብ መጠየቅ እንዲችሉ መብት ተጠብቆላቸዋል፡፡

4. በዚህ ችሎት ለነበረዉ ክርክር የወጣዉን ወጭ ግራ ቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

## <u>ትእዛዝ</u>

<u>ማስታወሻ</u>፡- ይህ የሰበር ችሎት ዉሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

1. በዉሳኔ ተራ ቁጥር 2 መሠረት እንዲያስፈጽም የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ግራ ቀኙ ሲጠይቁ ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠ እግድ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዝግቷል ፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 258429

የካቲት 28 ቀን 2017ዓ/ም

ዳኞች ፡- ገበየሁ ፈለቀ

አለማየሁ ሹናራ

ደረጀ አያና

ኑረዲን ከድር

ብርሃኑ መንግሥቱ

**አመልካች፡- አቶ መንገሻ መሮ :-ቀረቡ፡፡**

**ተጠሪዎች፡- 1፡- መ/ር መስፍን መንገሻ**

**2፡- አቶ አለሙ መንገሻ**

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ የፍርድ ተሰጥቷል፡፡

# ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ነሀሴ 09 ቀን 2016 ዓ.ም ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የእኔ እና ባለቤቴ የሆነውን ይዞታ በህይወት እያለሁ ልጆቼ ለሆኑት ተጠሪዎች እንዳካፍል በደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 14337 በነሀሴ 18 ቀን 2015 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 14740 ህዳር 25 ቀን 2016 ዓ.ም ይህንኑን ውሳኔ በማጽናቱ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በሚል ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በዴቻ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን በአሁን አመልካች እና በቀድሞ ባለቤታቸው መካከል የነበረው ትዳር በፍቺ መጠናቀቁን ተከትሎ ንብረታቸውን ተከፋፍለው እንዲቀርቡ በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ለመካፈል ሲሉ ተጠሪዎች ንብረቱን አናካፍልም በማለት ወደ ክርክሩ በመግባት የጣልቃ ገብ

አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡የአቤቱታቸውም ይዘት በአጭሩ ግራቀኙ የሚከራከሩበትን መሬት ከ2000 ዓ.ም ጀምሮ ኮረሪማ እና ቡና ተክለን እስካሁን ድረስ የምንጠቀምበት ስለሆነ ሊካፈሉ አይገባም የሚል ነው፡፡ አመልካችም መሬቱን በሽያጭም ሆነ በስጦታ ለተጠሪዎች ያላስተላለፍኩላቸው በመሆኑ የግል ርስቴን መካፈል አይችሉም በሚል ተከራክረዋል፡፡ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ማስረጃ በመስማት የክርክር መነሻ የሆነው ግማሽ ሄክታር ቡና እና ግማሽ ሄክታር ኮሮሪማ የአመልካች እና የባለቤታቸው የጋራ ንብረት ነው በሚል ወስኗል፡፡

ተጠሪዎችም በተሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታቸውን ለከፋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታው ተቀባይነት ባለማግኘቱ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡በአመልካቾች የይግባኝ አቤቱታው የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ተጠሪዎች ከወላጆቻቸው ይዞታ በመውሰድ በራሳቸው ጉልበት እና ገንዘብ ያለሙ እና ለምርትም ሲደርስ ለአመልካች እና ባለቤታቸው እኩል በማካፈል በጋራ ሲጠቀሙ የነበሩ በመሆናቸው እንዲሁም የቤተሰብ አባል በመሆን በቤተሰብ በተመዘገበ ይዞታ ላይ እየተጠቀሙ የነበሩ በመሆናቸው የመጠቀም መብታቸው ቀሪ ሊሆን እና ያፈሩትንም ንብረት ሊያጡ አይገባም፣የስር ፍ/ቤቶችም ተጠሪዎች በይዞታው ላይ መብት የላቸውም በማለት የሰጡት ውሳኔ ተጠሪዎች በይዞታው ላይ ካላቸው መብት እና የቤተሰብ አባልነት አኳያ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውም ይዞታው ላይ የሚገኝ ቡና እና ኮረሪማ ባልና ሚስቱ ሊካፈሉ አይገባም፣አመልካች እና ባለቤታቸው ከተጠሪዎች ጋር በጋራ ሊጠቀሙ ይገባል በሚል ወስኗል፡፡ አመልካችም የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በሚል ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን አቤቱታው የቀረበለት ችሎትም ውሳኔው የህግ ስህተት አልተፈጸመበትም በማለት ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡

አመልካችም ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ በአጭሩ ተጠሪዎች በውል ወይንም በውርስ ያገኙት የይዞታ ባለቤትነት መብት ሳይኖራቸው መከራከራቸው በህገ መንግስት አንቀጽ 40/7/8 የተቀመጠውን መብት ጥሰት ነው፡፡ተጠሪዎች መሬቱን ከ2000 ዓ.ም ጀምረው አልምተውታል ቢባል እንኳን አባታቸውን ስላገዙ የባለቤትነት መብት አይሰጣቸውም፡፡የክርክር መነሻ የሆነውን ይዞታ ያገኘሁት በአዋጅ ቁጥር 110/99 መሰረት አርሶአደር በመሆኔ ሲሆን ተጠሪዎች የከተማ ነዋሪዎች እና የመንግስት ሰራተኞች በመሆናቸው በውርስም ከሆነ ከሞትኩ በኃላ የሚፈፀም ይሆናል እንጂ በህይወት እያለው ይዞታውንና ንብረቱን ሊካፈሉ አይችሉም በሚል የተሰጠው ውሳኔ እንዲታረም ጠይቀዋል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም ተጠሪዎች የአመልካች ልጆች ሆነው ፍቺን ተከትሎ በአመልካች እና በባለቤታቸው መካከል በነበረው የባል እና የሚስት የጋራ ንብረት ክፍፍል ክርክር በጣልቃ በመግባት የክርክር መነሻ የሆነውን ንብረት ከወላጆቻቸው ጋር በጥገኝነት ሲጠቀሙበት የነበረ ስለመሆኑ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት እንዲካፈሉ የተወሰነበት አግባብ ወላጆች በህይወት ባሉበት ተወላጆቻቸው ንብረት ላይ

ከሚኖራቸው የመብት አድማስ አንጻር ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባው መሆኑን በመጥቀስ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪዎችም ነሐሴ 09 ቀን 2016 ዓ.ም በሰጡት መልስ አመልካች በ2000 ዓ.ም በምስክሮች ፊት ሌላ ቦታ ሄዳችሁ የጉልበት ስራ ከምትሰሩ የራሴ አንድ ሄክታር ይዞታ ላይ ቡና እና ኮረሪማ ተክላችሁ ለኔ ግማሹን እናንተ ደግሞ ግማሹን ለሁለት ተጠቀሙ በማለት ሰጥቶናል፡፡በዚህም መሰረት ማንም ሳይቃወመን በራሳችን ጉልበት እና ገንዘብ በመሬቱ ላይ ቡና እና ኮሮሪማ አልምተን ለአመልካችም አላባውን ግማሽ በማካፈል እየተጠቀምንበት እንገኛለን፡፡በስር ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔም የክርክር መነሻ የሆኑትን ንብረት እንደቀደመው በጋራ ተጠቀሙ የሚል እንጂ አመልካችን ከይዞታው የሚያፈናቅል አይደለም፡፡በስር ፍርድ ቤት ተከራካሪ የነበሩት አመልካች እና ባለቤታቸው ወ/ሮ ወርቅነሽ ገብሬ ከአመልካች ጋር ፍቺ የፈጸሙት ባለቤታቸው የተሰጠውን ውሳኔ ያልተቃወሙ ሲሆን አመልካች በበኩላቸው ያለምንም ውክልና ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት ያለው አይደለም፣አመልካች እና ባለቤታቸው በስር ፍርድ ቤት የክርክር መነሻ ሆነውን ንብረት በጋራ ስንጠቀም አልነበርንም በሚል ያቀረብነውን አቤቱታ በማስረጃ ባላስተባበሉበት ንብረቶቹ የጋራ ሊሆን አይገባም በሚል ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት ያለው ባለመሆኑ የቀረበው የሰበር አቤቱታ ውድቅ ተደርጎ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ እንዲጸናልን በሚል ተከራክረዋል፡፡

አመልካችም መስከረም 29 ቀን 2017 ዓ.ም ባቀረቡት የመልስ መልስ ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታቸውን አጠናክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና የግራ ቀኙ ክርክር በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን እኛም አቤቱታ ከቀረበበት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች እና ከማስቀረቢያ ነጥብ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡እንደመረመርነዉም በስር ደቻ ወረዳ ፍርድ ቤት አመልካች የነበሩት ወ/ሮ ወርቅነሽ ገብሬ በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ የትዳር ፊቺን ተከትሎ የፊቺው ውጤት የሆነውን ንብረት እንዲያካፍሏቸው የሚል ሲሆን ተጠሪዎች በክርክሩ ጣልቃ በመግባት አመልካች እና ባለቤታቸው የሚከራከሩበት ግማሽ ሄክታር ቡና እና ግማሽ ሄክታር ኮሮሪማ በሚመለከት ተክለን አብረን ስንጠቀም የቆየን ቢሆንም አመልካች እና ባለቤታቸው በ2000 ዓ.ም በመፋታታቸው የሚከራከሩበት ንብረት የኛ ስለሆነ ሊካፈሉ አይገባም የሚል ነው፡፡አመልካችም በተጠሪዎች በቀረበው የጣልቃ ገብነት አቤቱታ ላይ በሰጡት መልስ ተጠሪዎች ግማሽ ሄክታር ቡና እና ግማሽ ሄክታር ኮሮሪማ የኛ ነው በሚል ያቀረቡትን አቤቱታ በተመለከተ በስጦታም ይሁን በሺያጭ አላስተላለፍኩላቸውም፣ከእናታቸው ጋር በመሆን ንብረት የተካፈሉ በመሆናቸው ንብረቴን ሊካፈሉ አይችሉም በሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡የስር ፍርድ ቤት አመልካች ነበሩና የትዳር ፍቺን ተከትሎ አመልካች ንብረቱን እንዲያካፍላቸው አቤቱታ ያቀረቡት የአመልካች ባለቤት በበኩላቸው ንብረቱ የማይመለከተኝ ስለሆነ ተጠሪዎች አመልካችን ከሰው መውሰድ ይችላሉ በሚል መልስ

ሰጥተዋል፡፡ፍርድ ቤቱም በተጠሪዎች የቀረቡትን ምስክሮች በመስማት የክርክር መነሻ የሆነው ግማሽ ሄክታር ቡና እና ግማሽ ሄክታር ኮሮሪማ የአመልካች እና የባለቤታቸው የጋራ ንብረት ነው በሚል የወሰነ ስለመሆኑ የሚያስገነዝብ ነው፡፡

አመልካች በስር ፍርድ ቤት አስቀድመው ሲከራከሩ የነበሩት የክርክር መነሻ በሆነው ይዞታ ላይ የሚገኘው ቡና እና ኮሮሪማ ተክል የግል ንብሬቴ ስለሆነ ተጠሪዎች መካፈል አይችሉም የሚል ሲሆን የወረዳው ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ንብረቱ የአመልካች የግል ንብረት መሆኑን ሳይሆን የጋብቻ ፍቺን ተከትሎ በቀረበው የንብረት ክፍፍል መሠረት የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ነው የሚል ነው፡፡ አመልካችም የተሰጠውን ውሳኔ በይግባኝ ያስለወጡ ስለመሆኑ የቀረበ ነገር የለም፡፡ተጠሪዎች በተሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታቸውን ለደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የክርክር መነሻ የሆነውን ቡና እና ኮሮሪማ በተመለከተ ተጠሪዎች ይዞታውን ከአመልካች እና ባለቤታቸው በመውሰድ ቡና እና ኮሮሪማ በገንዘባቸው እና ጉልበታቸው በማልማት ንብረቶቹ ለምርት ሲደርሱ በጋራ ሲጠቀሙ የነበሩ ስለመሆናቸው ተረጋግጧል፤አመልካችም ይህንን በማስረጃ አላስተባበሉም በሚል ተጠሪዎች እንደቀደመው ንብረቶቹን በጋራ እንዲጠቀሙ በሚል የተወሰነ ስለመሆኑ የሚያሳይ ነው፡፡በመሆኑም አመልካች በአንድ በኩል የክርክር መነሻ የሆነው ንብረት የግል ንብረቴ ነው በሚል የሚከራከሩ ሲሆን በሌላም በኩል ንብረቶቹ እንደተባለው የግል ሀብታቸው ሳይሆን የአመልካች እና የባለቤታቸው የጋራ ሀብት ነው በሚል የተወሰነ ሆኖ እያለ ይህንን ውሳኔ ያላስለወጡ ከመሆናቸውም በላይ የስር ፍርድ ቤት ከሰሽ የነበሩትና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት 2ኛ ተጠሪ የነበሩት ወ/ሮ ወርቅነሽ ገብሬም በተሰጠው ውሳኔ እንዲለወጥ የሰበር አቤቱታ አላቀረቡም፤አመልካችም የሰበር አቤቱታ እንዲያቀርቡ ውክልናም ስለመስጠታቸው የቀረበ ማስረጃ የለም፡፡ስለሆነም አመልካች በፍቺ ከተለያዩት ከቀድሞ ባለቤታቸው ውክልና ሳይሰጣቸው በስር ወረዳ ፍርድ ቤት በተሰጠው ውሳኔ መሠረት ንብረቶቹ የባልና የሚስት የጋራ ሀብት ነው በሚል የተሰጠው ውሳኔ እንዲጸናልኝ በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

ሆኖም ከላይ እንደተመለከተው የክርክር መነሻ የሆኑ የቡና እና ኮሮሪማ ንብረቶች በተጠሪዎች የተፈራው በአመልካች እና ባለቤታቸው የጋራ ይዞታ ላይ ስለመሆኑ ያላከራከረ ቢሆንም መሬት የመንግስትና የህዝብ ሀብት ሆኖ ማናቸውም ኢትዮጵያ አርሶ አደር የመሬት ባለይዞታ የመሆንና በመሬት ይዞታቸው የመጠቀምና ከይዞታው ያለመፈናቀል መብት ያለው መሆኑ በህገመንግስቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀፅ 4 በግልፅ ተደንግጓል፡፡መንግስት የአርሶ አደሮችን የመሬት ባለይዞታ የመሆን፣በመሬቱ የመጠቀምና ከይዞታቸው ያለመፈናቀል መብት ህጋዊና ተግባራዊ ለማድረግ የፌዴራል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 456/93 እና አዋጁን የተካው አዋጅ ቁጥር 1324/2016 እንደዚሁም በክልል ደረጃ በደቡብ ክልል አዋጅ ቁጥር 110/1999 በማውጣት

ተግባራዊ እየተደረገ የሚገኝ ነው፡፡በዚህ መሠረት አመልካች የክርክር መነሻ የሆነው ቡና እና ኮሮሪማ በተጠሪዎች ጉልበት እና ገንዘብ የተፈራ ስለመሆኑ ያላስተባበሉ ቢሆንም የክርክር መነሻ የሆኑ ቡና እና ኮሮሪማ የተፈራበት የመሬት ይዞታው የአመልካች እና የባለቤታቸው ይዞታ ሆኖ በስማቸው የተመዘገበና ግብርም የሚከፍሉበት በመሆኑ ተጠሪዎች በይዞታው ላይ ያላቸው መብት በይዞታው ላይ ያፈሩትን ንብረት ከወላጆቻቸው ጋር አብረው የመጠቀም መብት በቀር ንብረቶቹ ያለበትን የመሬት ይዞታ ላይ መብት የሚሰጣቸው ባለመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባለይዞታዎቹን በሚያፈናቅል መልኩ ተጠሪዎች በይዞታው ላይ ከተፈራው ንብረት ከይዞታው ጭምር የጋራ እንደሆነ ተደርጎ የተወሰነበት አግባብ ተገቢ ሆኖ አላገኘንም፡፡

ሲጠቃለል ተጠሪዎች ከመሬት ባለይዞታንነት በመለስ ያለውን የክርክር መነሻ የሆነውን ግማሽ ሄክታር ቡና እና ግማሽ ሄክታር ኮሮሪማ በአመልካች ፈቃደኝነት በገንዘባቸው እና በጉልበታቸው በአመልካች እና በባለቤታቸው ይዞታ ላይ በማልማት ንብረቶቹ ለምርት ሲደርሱ በጋራ ሲጠቀሙ የነበሩ ስለመሆናቸው ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ በመሆኑ በአመልካች እና ባለቤታቸው መካከል የነበረው ጋብቻ በፍቺ ሲቋረጥ በዚህ ምክንያት ተጠሪዎች በንብረታቸው የመጠቀም መብት ሊቋረጥ የማይገባ ስለመሆኑ ተገቢ ቢሆንም ንብረቶቹን በጋራ የመጠቀም መብት የአመልካች እና የባለቤታቸውን የመሬት ባለይዞታንነት መብት ባላከበረ መልኩ የተሰጠው ውሳኔ በአዋጁ አንቀጽ 2(4)(ሀ) እና 10(1)(ሐ) መሠረት መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 14740 ህዳር 27 2016 ዓ.ም በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 14337 ነሐሴ 18 ቀን 2015 ዓ.ም የተሰጠውን ቤት ውሳኔ በማጽናት የሰጠው ውሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2012 አንቀጽ 9(1)(ለ) መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪዎች የክርክር መነሻ የሆነውን ንብረት በጋራ መጠቀም ንብረቱ የሚገኝበትን የመሬት ባለይዞታንነት መብት የሚያጎናጽፋቸው አይደለም ብለናል፡፡ የመሬት ይዞታው የአመልካች እና የስር ፍርድ ቤት አመልካች ነው ብለናል፡፡
3. አመልካችና ተጠሪዎ በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፣ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

መ/ዐ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት


የሰ/መ/ቁ 259234

የካቲት 25 ቀን 2017ዓ/ም

ዳኞች፡-ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ብርቅነሽ አሱባለው

**አመልካች፡-** አቶ ሳሙኤል ድረስ ደመቀ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ዳሽን ባንክ አ.ማ - ነ/ፈጅ መንገሻ ሲሳይ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍርድ**

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የካቲት 04 ቀን 2016 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 307535 ጥር 23 ቀን 2016 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የስራ ክርክርን የሚመለከት ሆኖ ክርክሩ የተጀመረው በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡በስር ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ሆነው ተከራክረዋል፡፡

አመልካች መጋቢት 20 ቀን 2015 ዓ.ም በተጻፈ ክስ በተጠሪ ባንክ ዉስጥ በምክትል ሥራ አስኪያጂነት የስራ መደብ ከሚያዝያ 24 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ በራሴ ፍቃድ የስራ ዉሉን


**ማስታወሻ፡** - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነ ድለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገ ለግልም!

እስካቋረጥኩበት ታህሳስ 17 ቀን 2015 ዓ.ም ጠቅላላ ብር 46,191.01(አርባ ስድስት ሺ አንድ መቶ ዘጠና አንድ ከ01/100) እየተከፈለኝ በቋሚነት ተቀጥሬ እሰራ የነበረ ሲሆን ስራዉን በገዛ ፍቃዴ ስለቅ ተጠሪ ሊከፍለኝ የሚገባዉን የተጠራቀመ ፕሮፊደንት ፈንድ፣ የአገልግሎት ክፍያ፣ የተጠራቀመ የአመት ፍቃድ፣ ጠቅላላ ብር 541,422.78(አምስት መቶ አርባ አንድ ሺ አራት መቶ ሃያ ሁለት ከ78/100) ሊከፍለኝ ስላልቻል ይህን ክፍያ እንዲከፍለኝ እንዲሁም ክፍያዉ ለዘገየበት የካሳ ክፍያ፣ ያለስራ ለተቀመጥኩበት የሶስት ወር ደመወዝ ካሳ እና የስራ ልምድ ከእዳ ነፃ ተብሎ እንዲሰጠኝ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡

ተጠሪ ሚያዝያ 05 ቀን 2015 ዓ.ም በተጻፈ መልስ አመልካች የስራ መሪ በመሆናቸዉ ጉዳዩ መታየት ያለበት በፍታብሄር ችሎት እንጂ በስራ ክርክር ችሎት አይደለም የሚል የመጀመርያ ደረጃ መቃወሚያ እና በፍሬ ጉዳይ ላይ ደግሞ የስራ ዉሉ ሲቋረጥ ሊከፈላቸዉ የሚገባዉ ክፍያዎች ያልተከለከሉ እና አመልካች እዳ የነበረባቸዉ በመሆኑ እዳቸዉ ተቀናሽ ተደርጎ ሊከፈላቸዉ እንደሚችል የተገለፀላቸዉ ቢሆንም ተቀናሽ ሊደረግ አይገባም በማለት ክፍያቸዉን ለመዉስድ ፍቃደኛ ባለመሆናቸዉ ልንጠየቅ አይገባም፣ ክፍያዎች የዘገየው በተጠሪ ጥፋት ሳይሆን አመልካች ተቀናሽ የተደረገ ክፍያ አልቀበልም በማለታቸዉ በመሆኑ በአመልካች በኩል የተጠየቀዉን ክፍያ በሙሉ ልንከፍል አይገባም፣ የስራ ልምድ አልተከለከሉም የሚፈለግባቸዉን ዕዳ ከፍለዉ መዉሰድ ይችላሉ በማለት በዝርዝር መልስ አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተጠሪ በኩል የቀረበዉን የመጀመርያ ደረጃ መቃወሚያ አመልካች ስራ መሪ አልነበሩም በማለት በብይን ዉድቅ ከደረገ በኃላ በፍሬ ጉዳይ ላይ የግራቀኝ ክርክር እና ማስረጃ ሰምቶ አመልካች ተቀናሽ መሆን የነበረባቸዉን ክፍያዎች ያመኑ በመሆኑ ባመኑት መሰረት ዕዳዉ ተቀንሶ የሚቀረዉን የተጣራ ብር 257,716.94(ሁለት መቶ ሃሳ ሺ ስባት መቶ አስራ ስድስት ከ94/100) ተጠሪ ለአመልካች ሊከፍል ይገባል፣ ተጠሪ አመልካች የሚገባዉን ክፍያ ዕዳዉን ተቀናሽ አድርጎ መክፈል በሚገባዉ ግዜዉ ዉስጥ ያልከፈለ በመሆኑ ክፍያዉ ለዘገየበት የአንድ ወር ደመወዝ ለአመልካች ሊከፍል ይገባል፣ አመልካች የጠየቁት ዉዝፍ ደመወዝ፣ የካሳ ክፍያ እና ሌሎች የክፍያ ጥያቄዎች የህግ መሰረት የሌለዉ ስለሆኑ ተጠሪ ሊጠየቅ አይገባም፣ አመልካች ዕዳቸዉን በተመለከተ ግዴታቸዉን ሳይወጡ ክሊራንስ ይሰጠኝ በማለት ያቀረቡት ጥያቄ አግባብነት የለዉም፣ ተጠሪ ለአመልካች በአሰሪና ሰራተኛ አዋጁ መሰረት የተዘጋጀ የስራ ልምድ ሊሰጥ ይገባል በማለት ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ተጠሪ በዚህ ብይን እና ዉሳኔ ላይ ቅር ተሰኝተዉ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱ በቀረበዉ ይግባኝ አቤቱታ ላይ ግራቀኙን አከራክሮ አመልካች ምክትል ስራ አስኪያጅ እንደነበሩ በክሳቸዉ የገለፁ እና ስራ መዘርዝራቸዉም ላይ ዕቅድ ማዘጋጀት እና መተግበር፣ የስራ ዕቅድና በጀት በማዘጋጀት ላይ መሳተፍና ሲፀድቅ ተግባራዊነቱን ማረጋገጥ፣ የሰራተኞችን መገኘት መቆጣጠርና መከታተል፣ የትርፍ ሰአት እና የዓመት እረፈት ማፅደቅ፣ የዲሲፒሊን እርምጃ የመዉሰድ ተግባራትን ያከናዉኑ የነበር መሆኑ የተረጋገጠ ሆኖ ሳለ የስር ፍርድ ቤት አመልካች የስራ መሪ አልነበሩም በማለት የመጀመርያ ደረጃ መቃወሚያዉን ዉድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነዉ፣ አመልካች ከላይ የተዘረዘሩ ተግባራትን ይፈፅሙ የነበር በመሆኑ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጁ መሰረት የስራ መሪ አልነበሩም የሚያስብል ባለመሆኑ ጉዳዩ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጁ መሰረት የሚሰተናገድ አይደለም በማለት የስር ፍርድ ቤት የሰጠዉን ብይን እና ዉሳኔ በመሻር ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች የካቲት 04 ቀን 2016 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይህን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ሲሆን ይዘቱም የስራ መሪ ማለት የስራ ባህሪይ በአሰሪው በተሰጠው የውክልና ስልጣን መሰረት የሥራ አመራር ፖሊሲዎችን የማውጣትና የማስፈጸም ተግባር እና ስልጣን ያለው ወይም ሰራተኛን የመቅጠር ፣የማዘዋወር፣ የማገድ፣ የማሰናበት ወይም የመመደብ ተግባሮችን የመወሰን ተግባር እና ስልጣን ያለው እንደሆነ እና እነዚህን የመሳሰሉት የሥራ አመራር ጉዳዮች አስመልክቶ የአሰሪውን ጥቅም ለመጠበቅ አሰሪው ሊወስደው ስለሚገባው እርምጃ በማንም ሳይመራ የራሱን የውሳኔ ሃሳብ የሚያቀርብ የህግ አገልግሎት ኃላፊን የሚጨምር መሆኑን በአዋጅ ቁጥር 1156/11 አንቀጽ 2(10) ላይ በግልጽ ተደንግጎ የሚገኝ እና ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 92466 በተመሳሳይ ትርጉም ሰጥቶበት እያለ የስር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይህን ድንጋጌ እና አስገዳጅ የህግ ትርጉም እንዲሁም በአመልካች በኩል የቀረበዉን የምክትል ስራ አስኪያጅ ወይም የደንበኞች አገልግሎት ሥራ አስኪያጅ የሚለውን የስራ መደብ ዝርዝር የቅጥር ሁኔታና የሥራ ተግባርና ኃላፊነት የሚገልጽ የሰነድ ማስረጃ በአግባቡ ሳይመለከት አመልካች ስራ መሪ ነበሩ በማለት የሰጠዉን ብይን መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል፣ በምክትል ስራ አስኪያጅ ወይም በሌላ አጠራር የደንበኞች አገልግሎት ስራ አስኪያጅ የሥራ መደብ ላይ በምሰራበት ወቅት የተሰጠኝ ዝርዝር ኃላፊነትና ተግባር በቅርንጫፍ ባንኩ ውስጥ ያሉትን የደንበኞች አገልገሎት ኦፊሰሮች እንቅስቃሴ በማስተባበር በቅርንጫፍ ባንኩ ለስራ አስኪያጁን ድጋፍ በማድረግ ለደንበኞች የላቀ አገልግሎት መስጠት ከቅርንጫፍ ባንኩ ገንዘብ

ያዥ ጋር በጋራ በመሆን የቅርንጫፍ ባንኩን ገንዘብ ማስተዳደር ሲሆን ይህ ደግሞ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/11 አንቀጽ 2/10 መሰረት የስራ መሪ የሚያስብል አይደለም፣ ተጠሪ የፈፀመዉ የዕዳ ቅነሳ ተግባር በአዋጁ አንቀጽ 59 (1) ከተደነገገዉ ዉጭ ነዉ በማለት ያቀረብኩት መከራከርያ ታልፎ በፅሁፍ ፍቃዴን ሳልገልጽ እዳ ተቀናሽ መደረጉ አግባብ አይደለም በማለት ያቀረብኩት መከራከርያም መታለፉ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነዉ፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ በሰበር ችሎት ተመርምሮ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ የስራ መሪ እንጂ ሰራተኛ ባለመሆናቸዉ በስራ ክርክር ችሎት ክስ ለማቅረብም ሆነ ችሎቱ ዳኝነት ለማግኘት የህግ አግባብ የለዉም በሚል የሰጠዉ ዉሳኔ በህግ አግባብ ተጣርቶ የተወሰነ መሆን አለመሆኑን ይህ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 92466፣ 116038፣ 117076 እና ሌሎች መዛግብት ላይ ከሰጠዉ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ዉሳኔዎች አንፃር ለማጣራ የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

ጥር 05 ቀን 2016 ዓ.ም ተጽፎ የቀረበው የተጠሪ መልስ ይዘትም አመልካች በባንኩ ዉስጥ በምክትል ስራ አስኪያጂነት(የደንበኞች አገልግሎት ስራ አስኪያጅነት) የስራ መደብ ላይ ሲሰራ እንደነበር በስር ፍርድ ቤት የታመነ እና የተረጋገጠ ጉዳይ ሲሆን በዚህ የስራ መደብ ላይ አመልካች በየጊዜዉ የቅርንጫፍ የስራ እቅድ ማዘጋጀት እና መተግበር፣ የቅርንጫፉን የስራ እቅድ እና በጀት በማዘጋጀት ላይ በመሳተፍ እና ሲፀድቅ ተግባራዊነቱን ማረጋገጥ፣ ሰራተኞችን መቆጣጠር፣ የትርፍ ሰአት እና የአመት እረፍት የማፅደቅ እና የዲሲፒሊን እርምጃዎችን የመዉሰድ ተግባራትን ይፈፅሙ የነበር መሆኑን በማስረጃ ያረጋገጥን በመሆኑ ይህም የአመልካች ተግባር በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀፅ 2(10) እና ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 92466 በሰጠዉ ትርጉም መሰረት የስራ መሪ መሆናቸዉን የሚያረጋግጥ በመሆኑ የስር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አመልካች የስራ መሪ ናቸዉ ጉዳዩ በስራ ክርክር ችሎት ሊታይ አይገባም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ በህግ አግባብ በመሆኑ የአመልካች ቅሬታ ዉድቅ ሆኖ የስር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አልተፈፀመበትም ተብሎ ይወሰንልን የሚል ነዉ፡፡

አመልካች ተጠሪ ባቀረቡት መልስ ላይ ጥር 13 ቀን 2017 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ በማቅረብ ቅሬታቸዉን አጠናክረዉ ተከራክረዋል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ዉሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ፣ ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እና ቅሬታው ለሰበር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ነጥብ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደሚቻለው አመልካች የሚከራከረዉ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጁ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 2(10) ላይ ለስራ መሪ የተሰጠዉን ትርጉም እናፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 92466 የሰጠውን ውሳኔ እንዲሁም በስራ መዘርዝር ለአመልካች የተሰጠዉን ሃላፊነት መዘርዝር ነዉ፡፡

በመሠረቱ የሥራ መሪ ማለት በሕግ ወይም እንደ የድርጅቱ የስራ ፀባይ በአሠሪው በተሰጠ የውክልና ስልጣን መሠረት የሥራ አመራር ፖሊሲዎችን የማውጣት የማስፈፀም ስልጣን ያለዉ ወይም ሠራተኛን የመቅጠር፣ የማዛወር፣ የማገድ፣ የማሰናበት ወይም የመመደብ ተግባሮችን የመወሰን ስልጣን ያለዉ ግለሰብ ሲሆን እነዚህን የሥራ አመራር ጉዳዮች አስመልክቶ የአሠሪዉን ጥቅም ለመጠበቅ አሠሪዉ ሊወስደዉ ስለሚገባዉ እርምጃ በማንም ሳይመራ የራሱን የዉሳኔ ሀሳብ የሚያቀርብ የሕግ አገልግሎት ኃላፊን ይጨምራል በሚል በአሠሪና ሠራተኛ አዋጁ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 2(10) ስር ተመልክቷል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ የሚየስገነዝበው ከላይ ከተገለጹት ተግባራት መካከል አንዱን ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ተግባራት የአሠሪዉን ጥቅም በማስጠበቅ ዓላማ የመፈጸም ስልጣን የተሠጠዉ የሥራ ኃላፊ የስራ መሪ መሆኑን የሚያመለክት በመሆኑ ሠራተኛው በአሰሪው መ/ቤት ወይም ተቋም እንዲያከናውን የተሰጠው ተግባር እና የሥራ ኃላፊነቶች እያንዳንዳቸው ምን ምን እንደሆኑ መመርመር የሚጠይቅ ነው፡፡ ሠራተኛው በተግባር ሥራዎችን እንዳያከናዉን በአሠሪዉ መደረጉ ካልተረጋገጠ በቀር በሥራ ዉሉና በሥራ መዘርዘሩ ላይ የተሰጠዉን ኃላፊነት ሥራዉ አልፎ አልፎ የሚሠራ በመሆኑ ወይም ሥራዉ ሳያጋጥመዉ የቀረ የሥራ መሪ ሠራተኛ እንጂ የሥራ መሪ አይደለሁም በማለት የሚያቀርበዉ መከራከሪያ ተገቢነት ያለው አይሆንም፡፡ በዚህ ሁኔታ ሰራተኛዉ የሥራ መሪ መሆኑ ከተረጋገጠ ደግሞ የስራ ዉል ግንኙነት በአዋጁ አንቀጽ 3(2)(ሐ) እንደተመለከተው ከአሰሪና ሰራተኛ አዋጁ ተፈጻሚነት ወሰን ዉጭ ስለሆነ ጉዳዩ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅም ሆነ በስራ ክርክር ችሎት የሚታይ አይደለም፡፡

በዚህም መሰረት ወደ ተያዘው ጉዳይ ተመልሰን ስንመለከተው አመልካች የዳሽን ባንክ ውስጥ በምክትል ስራ አስኪያጅ ወይም የደንበኞች አገልግሎት ሥራ አስኪያጅ የሥራ መደብ ላይ ተመድቦ ስሰራ እንደነበር እና የዚህን ስራ መደብ ተግባራትን ሲያከናውን የነበረ ስለመሆኑ የስራ መዘርዝር መሰረት በማድረግ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ እና በአመልካች የተካደ አይደለም፡፡ በስራ

መዝርዝሩ ላይ ከተመለከቱት ዋና ዋና ተግባራት መካከል ዕቅድ ማዘጋጀት እና መተግበር፣ የስራ ዕቅድና በጀት በማዘጋጀት ላይ መሳተፍና ሲፀድቅ ተግባራዊነቱን ማረጋገጥ፣ የሰራተኞችን መገኘት መቆጣጠርና መከታተል፣ የትርፍ ሰአት እና የዓመት እረፊት ማፅደቅ፣ የዲሲፒሊን እርምጃ የመዉሰድ ተግባራትን ያከናዉኑ የነበር መሆኑ ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት ተመልክቷል፡፡ አመልካች የሚለው  የደንበኞች አገልገሎት ኦፊሰሮች እንቅስቃሴ በማስተባበር በቅርንጫፍ ባንኩ ለስራ አስኪያጁን ድጋፍ በማድረግ ለደንበኞች የላቀ አገልግሎት መስጠት ከቅርንጫፍ ባንኩ ገንዘብ ያዥ ጋር በጋራ በመሆን የቅርንጫፍ ባንኩን ገንዘብ ማስተዳደር ላይ የተወሰነ ነው በማለት ነው፡፡

በእርግጥ ሠራተኛዉ የሥራ መሪ ነዉ ወይስ አይደለም የሚለዉን ለመለየት በሕጉ የተቀመጠዉ መስፈረት አመላካች ዝርዝሮች መሆናቸዉን የሚያሳየዉ እንደደርጅቱ የስራ ጠባይ የሚለዉ ቃል ገላጭ ከመሆኑም በተጨማሪ የፖሊሲ ጉዳዮችን የሚመለከተዉ ጉዳይ ላይ መወሰን አለመወሰን እና የሰራተኛ ጉዳይ ላይ የመወሰን ስልጣን መኖር አለመኖሩ በተናጠል የሚታይ አንጂ በአንድነት የሚታዩ መስፈርቶች አይደሉም፡፡ እንዲሁም ደግሞ አመልካች በተግባር ሥራዎችን እንዳያከናዉን በተጠሪ መደረጉ ካልተረጋገጠ በቀር በሥራ መዘርዘሩ ላይ የተሰጠዉን ኃላፊነት ሥራዉ ሳያጋጥመዉ መቅረቱን መሰረት በማድረግ ወይም አመልክች በአቤቱታቸው እንደገለጹት ለስራ አስኪያጁን ድጋፍ ከማድረግ  ከቅርንጫፍ ባንኩ ገንዘብ ያዥ ጋር በጋራ  ገንዘብ ማስተዳደር ላይ የተወሰነ ነበር ስለሆነም ሠራተኛ እንጂ የሥራ መሪ አይደለሁም በሚል የሚያቀርቡ መከራከሪያዎች ተገቢነት ያለው አያደርገውም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሰበር ችሎቱ በተለያዩ መዝገቦች በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ እንዳመላከተዉም የስራ መሪነት የሚወሰነዉ በሕጉ ከተዘረዘሩት ሃላፊነቶች አኳያ ለሰራተኛዉ በሥራ መዘርዝሩ የተሰጠዉ ሃላፊነት ወይም በተግባር ያከናወናቸዉን ስራዎች በመመለከት እንደሆነ ነዉ፡፡ (ሰበር መ/ቁ/ 92466፣116038፣ 117076 እና ሌሎችም መዝገቦችን ተመሳሳይ ትርጉም የተሰጠበት ነው)፡፡

ስለሆነም ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች የስራ መሪ ነው በማለት የሰጠዉ ፍርድ የተጠሪን የስራ መዘርዝር ለአመልካች የተሰጠዉን ሃላፊነት እና የስራ መሪ የሚያሰኙ መስፈርቶች በሚመለከት በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁ/1156/2013 አንቀጽ 2/10/ ስር የተሰጠዉን ትርጉም እንዲሁም ሰበር ችሎቱ የሰጠዉን ውሳኔ መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በቀር መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አልተገኘም ፡፡ በዚሁ መሰረት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ውሳኔ**

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 307535 ጥር 23 ቀን 2016 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1//ሀ/መሰረት መሰረት ጸንቷል ፡፡
2. አመልካችና ተጠሪ በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

**<u>መዝገቡ ተዘግቷል</u>**፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

**<u>ማስታወሻ</u>**፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
## የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መቁ 259817

የካቲት 28 ቀን 2017ዓ/ም

ዳኞች፡ ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ብርቅነሽ እሱባለው

**አመልካች፡-** አቶ አሸናፊ ተስፋዬ. - ቀረበ

**ተጠሪ፡-** የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የብሄራዊ መረጃ እና ደህንነት አገልግሎት ነ/ፈ ሲራክ ፀጋዬ

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## <u>ፍርድ</u>

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የካቲት 15 ቀን 2016 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አስተዳደር ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 158/16 በቀን 21/05/2016 ዓ.ም የሰጠው ብይን ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ጉዳዩ የመንግስት ሰራተኛ በመስሪያ ቤቱ በተሰጠ ዉሳኔ ላይ ለአስተዳደር ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ የሚችልበት ሁኔታ እና የጊዜ ገደብ የሚመለከት ነዉ፡፡

በኢ.ፌ.ድ.ሪ የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አስተዳደር ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር አመልካች አመልካች ተጠሪ ተጠሪ ነበሩ፡፡ አመልካች በቀረበባቸው ክስ ከባድ የዲስፕሊን ጥፋት ፈፅመዋል ተብሎ ከሥራ እንዲሰናበቱ ውሳኔ የተሰጠባቸው እና በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ለአስተዳደር ፍርድ ቤት ይግባኝ ከማቅረባቸው በፊት የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜው ያለፈባቸው መሆኑን በመግለፅ ይግባኙ እንዲፈቀድላቸው የይግባኝ ማስፈቀጃ አቅርበው ውድቅ በመደረጉ የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው፡፡

አመልካች ህዳር 24 ቀን 2016 ዓ.ም በተፃፈ ክስ በተጠሪ መስሪያ ቤት ከባድ የዲስፕሊን ክስ ቀርቦባቸው ጥቅምት 9 ቀን 2015 ዓ.ም ጥፋተኛ የተባሉና በዚህም ቅር ተሰኝተው የይግባኝ አቤቱታ እያዘጋጁ እያለ በዚሁ ጥፋተኛ በተባሉበት ድርጊት ጥቅምት 24 ቀን 2015 ዓ.ም ተይዘው በማረሚያ ቤት ለ 11 ወር ከ 7 ቀን በመታሰራቸው ምክንያት እንዲሁም ባለቤታቸው በኦሮሚያ ክልል አርሲ ዞን የሚኖሩ እርጉዝና የልጆች አሳዳጊ በመሆናቸው ይግባኝ መጠየቅ ባለመቻላቸው የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ያለፈባቸው መሆኑን፣ ከእስር ጥቅምት 7 ቀን 2016 ዓ.ም ነፃ ተብለው ከተለቀቁ በኃላ ጥቅምት 21 ቀን 2016 ዓ.ም ተጠሪን ወደ ስራቸው እንዲመልሳቸው ቢጠይቁትም ምላሽ ያልሰጣቸው በመሆኑ በተጠሪ የተላለፈባቸው የስንብት ውሳኔ ላይ ይግባኝ ማቅረብ እንዲችሉ እንዲፈቀድላቸው የማስፈቀጃ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

ተጠሪ ታህሳስ 15 ቀን 2016 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች በማረሚያ ቤት የታሰሩ ቢሆንም ማንኛውም ታራሚ እንደሚደረግለት እገዛ እየተደረገላቸው ይግባኛቸውን በደንብ ቁጥር 77/1994 አንቀፅ 37(2) መሰረት በ 1 ወር ጊዜ ውስጥ ማቅረብ ይችሉ ነበር፡፡ በዲስፕሊን ከስራ የተባረሩት ጥቅምት 9 ቀን 2015 ዓ.ም ሲሆን ማረሚያ ቤት የገቡት ከ 15 ቀናት በኃላ ጥቅምት 24 ቀን 2015 ዓ.ም በመሆኑና በነዚህ ጊዜያት ይግባኝ ማቅረብ ሲችሉ ያላቀረቡ በመሆኑ ይግባኝ ለማቅረብም በዝግጅት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

ላይ የነበሩ ከሆነም ባለቤታቸው ይግባኙን ማቅረብ ይችሉ ነበር፡፡ እንዲሁም ከእስር እንደተፈቱ በ 15 ቀናት ውስጥ የይግባኝ ማስፈቀጃ ማቅረብ ይችሉ የነበረ ቢሆንም አመልካች ግን ከእስር ጥቅምት 7 ቀን 2016 ዓ.ም ተፈተው የይግባኝ ማስፈቀጃ ያቀረቡት 1 ወር ከ 15 ቀን ካለፈ በኃላ ህዳር 24 ቀን 2016 ዓ.ም በመሆኑ መብታቸው በይርጋ ታግዷል፡፡ በሌላ በኩልም በደንብ ቁጥር 77/94 አንቀፅ 37(4) መሰረት የስራ ስንብት ወይም ከደረጃ ዝቅ ከመደረግ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች በማናቸውም ሁኔታ ከ 6 ወር በኃላ ይግባኝ ማቅረብ የማይቻልባቸው ሲሆን አመልካች ግን የይግባኝ ማስፈቀጃቸውን ያቀረቡት 1 አመት ከ 1 ወር ካለፈ በኃላ በመሆኑ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት መልሱን አቅርቧል፡፡

የኢፌዲሪ የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አስተዳደር ፍርድ ቤትም አመልካች በተጠሪ የስራ ስንብት ውሳኔ ጥቅምት 9 ቀን 2015 ዓ.ም፣ እስር ቤት የገቡት ጥቅምት 24 ቀን 2015 ዓ.ም እንዲሁም ከእስር የተፈቱት ጥቅምት 7 ቀን 2016 ዓ.ም ከ 1 አመት በላይ ቆይተው ሲሆን በነዚህ ጊዜያት በወንጀል ተጠርጥረው ማረሚያ ቤት የነበሩ በመሆኑ ይግባኝ ለማቅረብ የሚችሉበት እድል እንዳልነበረ መረዳት ይቻላል፡፡ ነገር ግን ከእስር ጥቅምት 7 ቀን 2016 ዓ.ም ከተፈቱ በኃላ በስነ ስርአት ህጉ መሰረት ይግባኛቸውን በ 15 ቀናት ማቅረብ ሲገባቸው ከእስር ከተፈቱ በኃላ ከ 1 ወር ከ 15 ቀናት በኃላ ህዳር 24 ቀን 2016 ዓ.ም ማቅረባቸውና ለዚህም በቂ ምክንያትና ማስረጃ ያላቀረቡ በመሆኑ በፌዴራል የመንግስት ሰራተኞች የዲስፕሊን አፈፃፀምና የቅሬታ አቀራረብ ደንብ ቁጥር 77/1994 አንቀፅ 37(4) መሰረት የቀረበው የይግባኝ ማስፈቀጃ ውድቅ ተደርጓል በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ብይን ቅር በመሰኘት ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የካቲት 15 ቀን 2016 ዓ.ም ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይዘቱም ከማረሚያ ቤት ከእስር ጥቅምት 7 ቀን 2016 ዓ.ም እንደተፈቱ ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሄድ የውሳኔ ግልባጭ እንዲሰጣቸው ጠይቀው በፍርድ ቤቱ ነፃ የተባሉበት ውሳኔ ከ 8 ቀን በኃላ በ 15/02/2016 ዓ.ም ተሰጥቷቸው ውሳኔውን በመያዝ በ 14 ቀናት ውስጥ ተጠሪ ወደ

ስራቸው እንዲመልሳቸው በፅሁፍ አስፈርመው የሰጡና በተደጋጋሚ እየሄዱ ሲጠይቁ ኃላፊ የለም፣ ኃላፊዎች ስብሰባ ላይ ናቸው፣ ጉዳዩ በኮሚቴ ነው የሚታየው፣ ኮሚቴ አልተሰበሰበም በማለት አቤቱታቸውን በጊዜው እንዳያቀርቡ እያደረጓቸው መሆኑን ህዳር 21 ቀን 2016 ዓ.ም እንደተረዱ ህዳር 24 ቀን 2016 ዓ.ም በ 3 ቀናት ውስጥ ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አስተዳደር ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም የይግባኝ ጊዜው ያለፈ በመሆኑ ማስፈቀጃ አቅርቡ ተብለው ማስፈቀጃ ባቀረቡበት ሁኔታ እንዲሁም ለተጠሪ ከእስር ከወጡ በኃላ በ 14 ቀናት በፍርድ ቤት ነፃ መባላቸውን የሚያስረዳ ውሳኔ በመያዝ ተጠሪ ወደ ስራቸው እንዲመልሳቸው አስፈርመው መስጠታቸው ዳተኛ አለመሆናቸውን የሚያሳይ ሆኖ እያለና ሰበር በመዝገብ ቁጥር 62452 በቅፅ 13 እንዲሁም በመዝገብ ቁጥር 36730 ቅፅ 9 ላይ በዚህ ጉዳይ ላይ አስገዳጅ ውሳኔ ሰጥቶ ባለበትና በማስረጃ አስረድተው እያለ በማስረጃ አላስረዱም በማለት አስተዳደር ፍርድ ቤቱ ህገመንግስታዊ ፍትህ የማግኘት መብታቸውን በሚጥስ መልኩ በይርጋ ታግዷል በማለት ብይን መስጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ተሽሮ የስር ፍርድ ቤት በዋናው ጉዳይ አከራክሮ ውሳኔ እንዲሰጣቸው ትዕዛዝ ይሰጥልኝ በማለት የሰበር አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የቀረበውን የሰበር አቤቱታ ከስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔና ከተገቢው ህግ ጋር አጣምሮ በመመርመር የኢፌዴሪ የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አስተዳደር ፍርድ ቤት የአመልካችን የይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የሰጠውን ብይን አግባብነት አመልካች ለአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ካቀረቡት የይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ፤ ከፌደራል መንግስት ሰራተኞች የዲሲፕሊን አፈጻጸምና የቅሬታ አቀራረብ ስነርስርአት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 77/1994 አንቀጽ 37(4) ድንጋጌ፤ ከኢፌዴሪ ህገመንግስት አንቀጽ 37(1) ድንጋጌ እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 205584፣ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 325(1) እና 326(1) ድንጋጌዎችን በመጥቀስ ፍርድ ቤቶች ግዜው ያለፈበትን ይግባኝ እንዲቀርብ ለመፍቀድ ፈቃድ ጠያቂው የሚያቀርበውን ማስረጃ መመዘን እና መመርመር ያለባቸው መሆኑን፤

አንድ ጊዜው ያለፈበትን ይግባኝ ማስፈቀጃ የሚያቀርብ ይግባኝ ጠያቂ ይግባኙን ሳያቀርብ የቀረበትን ምክንያት በማስረጃ አስደግፎ ካቀረበ ሊፈቀድለት እንደሚገባ ከተሰጠው የህግ ትርጉም አንጻር አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ጉዳዩ በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 28(3) መሰረት ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

ተጠሪ ታህሳስ 14 ቀን 2017 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች በስር ፍርድ ቤት በወንጀል የተከሰሱበትን የውሳኔ ግልባጭ ለማውጣት 8 ቀን የፈጀባቸው እንዲሁም አስተዳደር መስሪያ ቤት ክስ ሊያቀርቡ ሲሄዱ የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ሬጅስትራር በቅድሚያ ለመስሪያ ቤቱ ወደ ስራ እንዲመልሱህ ጥያቄ አቅርብ ብለውኛል በማለት ያቀረቡት ክርክር በስር ፍርድ ቤት ያልቀረበ አዲስ ክርክር በመሆኑ ውድቅ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ለአመልካች የዲስፕሊን ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ማረሚያ ቤት እስከ ገቡበት ጊዜ ድረስ ይግባኝ ለማቅረብ የሚያስችል 15 ቀናት የነበሯቸው ሲሆን በነዚህ 15 ቀናት የይግባኝ አቤቱታ እያዘጋጁ ከነበረ ማረሚያ ቤት ሲገቡ በሚስታቸው አማካኝነት ይግባኝ መጠየቅ ሲችሉ ይህን ባላደረጉበት ሁኔታ ይህ ቢታለፍ እንኳን በማረሚያ ቤት በእስር ላይ በነበሩበት ጊዜም እንደማንኛውም እስረኛ ድጋፍ እየተደረገላቸው ይግባኝ ማቅረብ ሲችሉ እንዲሁም ከእስር ከወጡ በኃላም በ 15 ቀናት ውስጥ ማስፈቀጃ ማቅረብ ሲገባቸው 1 ወር ከ 15 ቀን ከሆነና ይህን መብት በዳተኝነት ካሳለፉ በኃላ የይርጋ ጊዜም እንደ አዲስ መቆጠር የሚጀምረው ዳተኛ ላልሆነና ተገቢውን ትጋት ላደረገ ወገን ሆኖ እያለ አመልካች ከአቅም በላይ የሆነ ችግር አጋጥሞኛ ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የሌለውና በአስተዳደር ፍርድ ቤቱ የተሰጠው ብይን መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት በመሆኑ ሊፀና ይገባል በማለት መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡

አመልካች ይህ መልስ ደርሷቸው ታህሳስ 22 ቀን 2017 ኢ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር አቅርበዋል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ፣ ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እና ቅሬታው ለሰበር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ነጥብ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደሚቻለው አመልካች ከባድ የዲስፕሊን ክስ ቀርቦባቸው ጥቅምት 9 ቀን 2015 ዓ.ም ጥፋተኛ የተባሉና በዚህም ቅር ተሰኝተው የይግባኝ ክርክር ላይ እያሉ ጥፋተኛ በተባሉበት ድርጊት ጥቅምት 24 ቀን 2015 ዓ.ም ተይዘው በማረሚያ ቤት እስከ ጥቅምት 7 ቀን 2016 ዓ.ም ቆይተው ነፃ ተብለው የተለቀቁ እና ጥቅምት 21 ቀን 2016 ዓ.ም ተጠሪን ወደ ስራቸው እንዲመልሳቸው የጠይቁ ቢሆንም ምላሽ ያልሰጣቸው በመሆኑ ጊዜው ያለፈው በእስር በመቆየታቸው እና ባለቤታቸው እርጉዝ የነበሩ በመሆኑ  ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት በመሆኑ ይግባኝ ማቅረብ እንዲችሉ እንዲፈቀድላቸው የሚጠይቅ ነው፡፡

በመሰረቱ በፌደራል መንግሥት ሠራተኞች የዲሲፕሊን አፈጻጸምና ቅሬታ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ቁጥር 77/1994 አንቀጽ 37(2) እንደሚያስገነዝበዉ በከባድ የዲስፕሊን ቅጣት ላይ ለአስተዳደር ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊቀርብ የሚችለዉ ዉሳኔዉ ለሠራተኛዉ በጽሁፍ በደረሰዉ በ30 ቀናት ዉስጥ ቢሆንም ይግባኙ በጊዜዉ ሳይቀርብ የዘገየዉ በአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከሆነ ከአቅም በላይ የሆነዉ ምክንያት ከተወገደበት ጊዜ ጀምሮ በ15 ቀን ዉስጥ ይግባኝ ለመቅረብ እንዲፈቀድለት ሊያመለክት እንደሚችል በዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 4 ስር ተደንግጓል፡፡ ይግባኙን በደንቡ በተመለከተው ጊዜ ባለማቅረባቸው ምክንያት ከፍርድ ቤቱ ፈቃድ ለማግኘት ጊዜው ካለፈ በኃላ ይግባኝ እንዲከፈት ጥያቄ የሚቀርበው በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 325 በተመለከተው ተመሳሳይ አግባብ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ ተቀባይነት ያለው መሆን አለመሆኑን የሚመረምረው በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 326 በተመለከተው መሰረት እንደየአግባቡ በንዑስ ቁጥር (1) ወይም (2) ነው፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማ አያገለግልም!

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች ከባድ የዲስፕሊን ጥፋት ፈጽሟል ተብሎ ከስራ እንዲሰናበት ተወስኖ የደረሰው ጥቅምት 09 ቀን 2015 ዓ.ም ቢሆንም ጊዜው ያለፈበት ይግባኝ ለማቅረብ እንዲፈቀድለት ለአስተዳደር ፍርድ ቤት አቤቱታ ያቀረበዉ ህዳር 24 ቀን 2016 ዓ.ም ሲሆን የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ማስፈቀጃ ጥያቄዉን ዉድቅ ያደረገዉ በ 15 ቀን ዉስጥ ለማቅረብ ያልቻለበትን በቂ ምክንያትና ማስረጃ አላቀረበም በሚል ስለመሆኑ የዉሳኔዉ ይዘት ያሣያል፡፡

የአመልካቹ ዋና መከራከሪያ ከማረሚያ ቤት ጥቅምት 7 ቀን 2016 ዓ.ም እንደተፈቱ ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ እንዲሰጣቸው ጠይቀው ከ 8 ቀን በኃላ ተሰጥቷቸው ውሳኔውን በመያዝ ተጠሪ ወደ ስራቸው እንዲመልሳቸው በፅሁፍ የጠየቁና በተደጋጋሚ እየሄዱ ሲጠይቁ በተጧቸው የተለያ ምክንያቶች አቤቱታቸውን በጊዜው እንዳያቀርቡ ያደረጓቸው መሆኑን እንደተረዱ ህዳር 24 ቀን 2016 ዓ.ም በ 3 ቀናት ውስጥ ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አስተዳደር ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ መሆኑን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህ ምክንያቶች ደግሞ በቀጥታ ለአስዳደር ፍርድ ቤቱ በተጠሪ መ/ቤት ውሳኔ መሰረት ይግባኝ አለማቅረቡን ሳይሆን ከቀረረበት ክስ በነጻ መሰናበታቸውን መሰረት በማድረግ ወደ ሥራ አሰሪው እንዲመልሳቸው ያቀረቡትን አቤቱታና የወሰደውን ጊዜ የሚመለከት እንጂ ይግባኙን እንዳያቀርቡ ያደረጋቸው መሆኑን የማያመለክቱ መሆኑን መሰረት በማድረግ የስር አስተዳደር ፍርድ ቤት በቂ ምክንያትና ማስረጃ አላቀረበም በማለት የቀረበውን ማስረጃ በመመርመር ያረጋገጠው መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

ሠራተኛዉ ለአስተዳደር ፍርድ ቤት ይግባኝ ለማቅረብ የሚችለዉ በደንቡ ላይ በተገለጹት ምክንያቶች እና ጊዜ ገደብ ዉስጥ መሆን እንዳለበት እሙን ነዉ፡፡ ከስንብት ዉሳኔ ጋር በተያያዘው ሰራተኛዉ ይግባኝ ለመቅረብ ያለዉ መብት የሚሰላው ከአቅም በላይ የሆነዉ ምክንያት ከተወገደበት ጊዜ ጀምሮ በመሆኑ አመልካች በእስር የቀየበት ጊዜ የተወገደው ወይም ከእስር የተለቀቀው ጥቅምት 7 ቀን 2016 ዓ.ም እና በ15 ቀን ዉስጥ ይግባኙን ያላቀረበ መሆኑን ከተረጋጋጠ ይግባኙን በተገቢው ጊዜ አላቀረበም

ለዚህም በቂምክንያት የለውም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ ከደንበ ቁጥር 77/1994 አንቀጽ 37(2)(4) ፡፡ በዚሁ መሰረት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ውሳኔ</u>

1. የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አስተዳደር ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 158/16 በቀን 21/05/2016 ዓ.ም የሰጠው ብይን በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1//ሀ/መሰረት መሰረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካችና ተጠሪ በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

<u>መዝገቡ ተዘግቷል</u>፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት**

የሰ/መ/ቁ 259947

*የካቲት 28 ቀን 2017 ዓ/ም*

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ

በእዉቀት በላይ

ሐፊዝ አባጆማል

ማርታ ተካ

አየለ ማሞ

አመልካች፡- አቶ ተስፋዬ ደገፋ - ቀረቡ፡፡
ተጠሪዎች፡- 1. ዶ/ር ትዕዛዙ ተፈራ

2. የኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 05 አስተዳደር ጽ/ቤት

3. የኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ጽ/ቤት

መዝገቡ የተቀጠረዉ የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ ተገቢዉን ለመስራት ሲሆን ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ይህ የሰበር መዝገብ ተከፍቶ ለዚህ ሰበር ችሎት የቀረበዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 224054 ጥር 30 ቀን 2016 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን ገልጸዉ አመልካች የካቲት 18 ቀን 2016 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸዉ ነዉ፡፡

ለዚህ የሰበር ክርክር ምክንያት የሆነዉ ክርክር የተጀመረዉ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን በከፍተኛዉ ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ፣ ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሾች በመሆን መከራከራቸዉን የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ ያመለክታል፡፡ ክርክሩ በማህበር በመደራጀት ከተገኘዉ ይዞታ ጋር የተያያዘ

ሲሆን አመልካች በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት ክስ በ03/08/1990 ዓ/ም ተመዝግቦ በፀደቀዉ የመተዳደሪያ ደንብ መሠረት የተደራጀ ታቦር የመኖሪያ ቤቶች ኀብረት ሥራ ማኀበር አባል በመሆን ተደራጅተዉ ማኀበሩ በሕጋዊ መንገድ ከመንግሥት ካገኘዉ ጠቅላላ ይዞታ ላይ መጠኑ 203.67 ካሬ ሜትር የሆነዉን የክርክሩን ይዞታ በድርሻ እንደሰጣቸዉና የዚሁ ይዞታ ሕጋዊ ባለመብት ስለመሆናቸዉም በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 281839 በኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ኀብረት ሥራ ጽ/ቤትና በኮልፌ ቀራኒዮ ክለ ከተማ የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ጽ/ቤት ላይ ክስ አቅርበዉ መብታቸዉ ተረጋግጦ ዉሳኔ እንዳገኙ፣ ሆኖም 1ኛ ተጠሪ ምንም ዓይነት ሕጋዊ መብት ሳይኖራቸዉ አቤቱታ ስላቀረቡ አመልካች በይዞታቸዉ ላይ ግንባታ እንዳያከናዉኑ 3ኛ ተጠሪ እንደከከለከላቸዉና 2ኛ ተጠሪም ለግንባታዉ ሥራ አስፈላጊ የሆኑትን እንደ ዉኃና የመብራት ቆጣሪ ያሉትን እንዳያስገቡ እንቅፋት እንደፈጠረባቸዉ፣ ከዚህም የተነሳ ግንባታዉን በወቅቱ ለማካሄድ ባለመቻላቸዉ ለግንባታ ቁሳቁሶች የዋጋ ንረት ከመጋለጣቸዉም ባሻገር ቤቱን ሠርተዉ ቢሆን ኖሮ አከራይተዉ ሊያገኙ ይችሉ የነበረዉን ገቢ እንዳጡ ገልፀዉ የተጠሪዎች ሕገወጥ ድርጊት ተወግዶ በፍርድ የተረጋገጠዉ መብታቸዉ እንዲከበርና ከተጠሪዎች ድርጊት የተነሳ የደረሰባቸዉን ኪሳራም ተጠሪዎች እንዲከፍሉ እንዲወሰንላቸዉ ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪዎች ለዚህ የአመልካች ክስ መልስ እንዲሰጡ በታዘዘዉ መሠረት ቀርበዉ 1ኛ ተጠሪ በዚህ ጉዳይ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 114966 በአመልካችና በ3ኛ ተጠሪ ላይ የበኩላቸዉን ክስ አቅርበዉ ጉዳዩ በክርክር ላይ ያለ በመሆኑ በአንድ ጉዳይ ላይ በሁለት ፍ/ቤቶች ክስ ሊቀርብ እንደማይገባ በመግለጽና ሌሎች የመቃወሚያ ነጥቦችንም በማካተት የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ በማቅረብና በአማራጭም ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ ይዞታዉ ታቦር ቁጥር 1 የመኖሪያ ቤቶች ኀብረት ሥራ ማኀበር በሚባለዉ 396 አባላት ባሉት ማኀበር በአባልነት ተደራጅተዉ ማኀበሩ የክርክሩን ይዞታ ሰጥቷቸዉ የያዙት እንጂ የአመልካች ይዞታ እንዳይደለ ገልፀዉ መልስ በመስጠት ተከራክረዋል፡፡ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በበኩላቸዉ ክርክር ያስነሳዉ ይዞታ አመልካች በታቦር የመኖሪያ ቤት ኀብረት ሥራ ማህበር በአባልነት ተደራጅተዉ የወሰዱት መሆኑንና 1ኛ ተጠሪ በአባልነት እንደተደራጁ የሚገልጹት ታቦር ቁጥር 1 የመኖሪያ ቤቶች ኀብረት ሥራ ማኀበር የተባለዉ ማኀበር ሀሰተኛና በሕገወጥ መንገድ የተደራጀ ማኀበር እንደሆነ ገልፀዉ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ከዚህ በኋላ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በ1ኛ ተጠሪ የቀረበዉን የክስ መቃወሚያ በብይን ዉድቅ በማድረግና በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተከፈተዉን መ/ቁጥር 114966 በከፍተኛዉ ፍ/ቤት ከተከፈተዉ መዝገብ ቁጥር 269292 ጋር በማጣመር በጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን ካከራከራቸዉ በኋላ የክርክሩ ይዞታ አመልካች በታቦር የመኖሪያ ቤቶች ኀብረት ሥራ ማኀበር በአባልነት ተደራጅተዉ ያገኙት ይዞታ ስለመሆኑ እንደተረጋገጠ ገልጾ 1ኛ ተጠሪ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 114966 ያቀረቡትን ክስ ዉድቅ በማድረግ እና አመልካች በክርክሩ ይዞታ ላይ በወቅቱ ግንባታ ሊያካሂዱ ካለመቻላቸዉ የተነሳ የደረሰባቸዉ ጉዳት ካለ ከጳጉሜ 1 ቀን 2012 ዓ/ም ጀምሮ ያለዉን ኪሳራ ሌላ ክስ አቅርበዉ የመጠየቅ መብታቸዉን በመጠበቅ ወስኗል፡፡

በመቀጠልም 1ኛ ተጠሪ በዚህ የከፍተኛዉ ፍ/ቤት ዉሳኔ ቅር ተሰተኝተዉ ይግባኝና አመልካች ደግሞ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት 1ኛ ተጠሪ ባቀረቡት ክስ ላይ ያቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ዉድቅ መደረጉንና ከፍተኛዉ ፍ/ቤትም ኪሳራዉን በተመለከተ የሰጠዉን ዉሳኔ በማስመልከት መስቀልኛ ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን የግራ ቀኙን ይግባኝና መስቀልኛ ይግባኝ የመረመረዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡትን ይግባኝ ተቀብሎ 1ኛ ተጠሪ በዚሁ ጉዳይ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክስ አቅርበዉ ጉዳዩ እየታየ ባለበት አመልካች ምናልባት ክስ አቅርበዉ ለማስከበር የሚፈልጉት መብት ካላቸዉም በዚያዉ መዝገብ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አቅርበዉ መብታቸዉን ሊያስከብሩ ሲገባ ክስ ቀርቦ ክርክር ላይ ባለ ጉዳይ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አዲስ ክስ ማቅረባቸዉና ከፍተኛዉ ፍ/ቤትም ይህንን ክስ ተቀብሎ አስቀድሞ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የቀረበዉን የክስ መዝገብ ወደ ራሱ በማዛወር ክሱ ከኋላ ከቀረበበት መዝገብ ጋር ማጣመሩ የፍ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 7፣ 8 እና 11 ድንጋጌዎችን የጣሰ እንደሆነ ገልጾ የከፍተኛዉን ፍ/ቤት ዉሳኔ በመሻርና አመልካች ያቀረቡትን መስቀልኛ ይግባኝ መመርመሩ አስፈላጊ አለመሆኑን በመግለጽ ክርክሩ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እንዲቀጥል በመወሰን ጉዳዩን ወደ ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መልሶታል፡፡

በመሆኑም አመልካች ይህ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ዉሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስለመሆኑ በአቤቱታቸዉ ላይ ያነሱት ዋና የቅሬታ ነጥብ 1ኛ ተጠሪ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ 2ኛ ተጠሪ ተከራካሪ ባለመሆኑ ተከራካሪ ባልሆነ ወገን ላይ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ለማቅረብ የማይቻል ከመሆኑም በላይ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ማቅረብ ለተከሳሽ በምርጫ የተተወ እንጂ ተከሳሽ በጉዳዩ ላይ በሌላ መዝገብ ክስ አቅርቦ መብቱን እንዳያስከብር የማይከለክል ሆኖ እያለ እንዲሁም የአመልካች ክስ የይዞታ መብትን ማስከበርን ብቻ ሳይሆን የሥረ ነገር የዳኝነት ሥልጣኑ ከፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የዳኝነት ሥልጣን በላይ የሆነ የገንዘብ ጥያቄን ጭምር ያካተተ ሆኖ ባለበት አመልካች በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ክስ ያቀረቡት ያለአግባብ እንደሆነ ተገልጾ የተሰጠዉ ዉሳኔ የፍ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 8(3)፣ 11፣ 30(1)፣ 36፣ 39 እና 234(1)(ረ) እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 81275፣ በሰ/መ/ቁጥር 102668 የሰጣቸዉን አስገዳጅ ዉሳኔዎችን የሚቃረን መሆኑን የሚዘረዝር ነዉ፡፡

ይህ የአመልካች የሰበር አቤቱታ በዚህ ሰበር ችሎት ተመርምሮ ተጠሪዎች ለአቤቱታዉ መልስ እንዲሰጡ ታዞ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች መጥሪያዉ ደርሷቸዉ ስላልቀረቡ መልስ የመስጠት መብታቸዉ የታለፈ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ በበኩላቸዉ ነሐሴ 14 ቀን 2016 ዓ/ም በጠበቆቻቸዉ አማካይነት ጽፈዉ በሰጡት መልስ አመልካች በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በተጠሪዎች ላይ ክስ ባቀረቡበት ጉዳይ 1ኛ ተጠሪ አስቀድሞ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአመልካችና በ3ኛ ተጠሪ ላይ ክስ አቅርበዉ ጉዳዩ በቀጠሮ ላይ ያለ በመሆኑና ክስ ቀርቦ በቀጠሮ ላይ ባለ ጉዳይ

ሌላ አዲስ ክስ ሊቀርብ የማይገባ ስለመሆኑ የፍ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 8 በግልጽ ስለሚደነግግ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ዉሳኔ ሕግን መሠረት ያደረገ እንጂ ስህተት የተፈጸመበት አለመሆኑን ገልጸዉ ዉሳኔዉ እንዲፀናላቸዉ በመጠየቅ ሰፋ ያለ ክርክር አቅርበዋል፡፡ አመልካችም የበኩላቸዉን ክርክር በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ አጠር ተደርጎ የተገለጸዉ ሲሆን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር አቤቱታዉ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ (የማስቀረቢያ ነጥብ) እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡

እንደመረመረዉም የዚህን ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ የሚሻ ዋናዉ የክርክር ነጥብ አመልካች በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በተጠሪዎች ላይ ክስ ማቅረባቸዉና ከፍተኛዉ ፍ/ቤት በዚሁ ጉዳይ ላይ 1ኛ ተጠሪ አስቀድሞ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአመልካና በ3ኛ ተጠሪ ላይ ክስ ያቀረቡባቸዉን መዝገብ ወደ ራሱ አስቀርቦ መዝገቦቹን አጣምሮ ክርክሩን መመርመሩ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን የሚመለከት ነዉ፡፡ በፍ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 7 ላይ እንደተደነገገዉ አንድ የፍትሐብሔር ክስ መታየት የሚገባዉ በአንድ የፍትሐብሔር ፍ/ቤት ብቻ ሲሆን አንዱን የፍትሐብሔር ክስ በአንድ ወይም ከአንድ በበለጡ ፍ/ቤቶች ለማቅረብ የሚቻል ሲሆን የክሱ ማመልከቻ በቀደምትነት የቀረበለት ፍ/ቤት ብቻ የዳኝነት ሥልጣን እንዳለዉ ተቆጥሮ ለክርክሩ ዉሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡ የዚህ ቁጥር ድንጋጌ ዋናዉ ዓላማ አንድ ጉዳይ በሁለት ወይም ከሁለት በላይ በሆኑ ፍ/ቤቶች ለየብቻዉ ታይቶ የተለያየ ይዘት ያላቸዉና ምናልባትም እርስ በርሳቸዉ የሚቃረኑ ዉሳኔዎች በጉዳዩ ላይ እንዳይሰጡ ለመከላል መሆኑ ግልጽ ነዉ፡፡ ነገር ግን ድንጋጌዉ አንድ የፍትሐብሔር ጉዳይ በአንድ ፍ/ቤት ብቻ ታይቶ ሊወሰን እንደሚገባ ከሚደነግግ በቀር በአንድ ጉዳይ ላይ በሁለት ፍ/ቤቶች ክስ ፈጽሞ እንዳይቀርብ የሚከለክል አይደለም፡፡ ይልቁንም የፍ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 7(2) ድንጋጌ በአንድ ጉዳይ ላይ በሁለት በተለያዩ ፍ/ቤቶች ክስ በቀረበ ጊዜ ክሱ ቀድሞ የቀረበለት ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን እንዳለዉ ተቆጥሮ ለክርክሩ ዉሳኔ ሊሰጥ እንደሚችል በመደንገግ በአንድ ጉዳይ ላይ በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ፍ/ቤቶች ክስ ሊቀርብ እንደሚችል ያስገነዝበናል፡፡ ነገር ግን የዚህ ንኡስ አንቀጽ ድንጋጌም ቢሆን በአንድ ጉዳይ ላይ በሁለት ፍ/ቤቶች ክስ በቀረበ ጊዜ ክሱ በቀደምትነት የቀረበለት ፍ/ቤት ክርክሩን ለማየት ሥልጣን እንዳለዉ ሊቆጠር እንደሚችል በፈቃጅነት ከመደንገጉ በቀር ባለሥልጣኑ ፍ/ቤት ክሱ ቀድሞ የቀረበለት ፍ/ቤት ብቻ ስለመሆኑ አስገዳጅ በሆነ መልኩ አይደነግግም፡፡ በመሆኑም በአንድ ጉዳይ ላይ በሁለት በተለያዩ ፍ/ቤቶች ክስ የቀረበ እንደሆነና ክሱ በቀደምትነት የቀረበለት ፍ/ቤት ከኋላ ላይ የቀረበዉን ክስንም ለመዳኘት የሥረ ነገር የዳኝነት ሥልጣን ያለዉ ከሆነ ክርክሩን የመዳኘት የቀደምትነት መብት ያለዉ በመሆኑ ጉዳዩ በአንድ ላይ ተጠቃሎ ክሱ በቀደምትነት በቀረበዉ ፍ/ቤት ሊታይ ይችላል፡፡ ነገር ግን ከኋላ የቀረበዉ ክስ ጉዳዩ አስቀድሞ ከቀረበለት ፍ/ቤት የሥረ ነገር የዳኝነት ሥልጣን በላይ የሆነ የዳኝነት ጥያቄን የያዘ ከሆነ በፍ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 7 ላይ የተደነገገዉ የቀደምትነት ሥልጣን ተፈጻሚ ሊሆን አይችልም፡፡ ምክንያቱም አንድ ፍ/ቤት ከሥረ ነገር የዳኝነት ሥልጣኑ በላይ የሆነዉን ጉዳይ አከራክሮ ሊወስን አይችልምና፡፡ የዚህ ዓይነቱ ሁኔታ

ካጋጠመ ደግሞ ሁለቱም ክሶች በፍ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 11 መሠረት በአንድ ላይ ተጣምረዉ ከክሶቹ ከፍተኛዉን ዋጋ (ግምት) የያዘዉን ክርክር ለመዳኘት የሥረ ነገር የዳኝነት ሥልጣን ባለዉ ፍ/ቤት ሊታዩ ይገባል።

አሁን በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች ለክርክሩ ምክንያት በሆነዉ ይዞታ ላይ እንዳላቸዉ የሚገልጹትን መብት ለማስከበር ከመጠየቅ ባሻገር ብር 600,000 (ስድስት መቶ ሺህ) የገንዘብ ጥያቄ ጭምር አካተዉ ክስ ያቀረቡ ስለመሆኑ በሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ ላይ በግልጽ የተመለከተ ከመሆኑም ባሻገር 1ኛ ተጠሪ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረቡት መልስም ይህንን ፍ ነገር አረጋግጠዋል። ይህ ከሆነ ደግሞ ክሱ በቀረበበት ወቅት በሥራ ላይ በነበረዉ አዋጅ መሠረት ከብር 500,000 (አምስት መቶ ሺህ) በላይ የሆነ የገንዘብ መጠንን የያዙ ክርክሮችን የመዳኘት የሥረ ነገር የዳኝነት ሥልጣን ያለዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመሆኑ አመልካች በጉዳዩ ላይ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ክስ ያቀረቡትም ሆነ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አስቀድሞ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት 1ኛ ተጠሪ አቅርበዉት የነበረዉን ክስ ወደራሱ በማዛወር ጉዳዮችን አጣምሮ ማየቱ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ሊባል የሚቻል አይደለም።

አመልካች የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ማቅረብ ሲገባቸዉ በጉዳዩ ላይ ሌላ አዲስ ክስ ማቅረባቸዉ አግባብ እንዳይደለ ተገልጾ በ1ኛ ተጠሪ የቀረበዉን ክርክርና በዚህ ረገድ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠዉን ዉሳኔ በተመለከተም እንደሚታወቀዉ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ የሚቀርበዉ በከሳሽነት ተሰይሞ በተከሳሽ ላይ ክስ ባቀረበዉ ሰዉ ላይ ብቻ እንጂ በተከሳሽነት አብሮ በተከሰሰ ሰዉ ላይ እና የክርክሩ ተሳታፊ ባልሆነ 3ኛ ወገን ላይ ጭምር አይደለም። ይህንን በተመለከተም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 102668 አስገዳጅ የሰበር ዉሳኔ ሰጥቷል። በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ክስ ያቀረቡት በ1ኛ ተጠሪ፣ 1ኛ ተጠሪ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከአመልካች ጋር በተከሳሽነት አጣምረዉ በከሰሱት የአሁን 3ኛ ተጠሪ እና በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በ1ኛ ተጠሪ በቀረበዉ ክስ ስሙ በከሳሽነትም ይሁን በተከሳሽነት ባልተጠቀሰዉ 2ኛ ተጠሪ ላይ ነዉ። በመሆኑም አመልካች በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተከሰሱበት መዝገብ በ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ላይ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ሊያቀርቡ ስለማይችሉ እነዚህን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ሊያቀርቡባቸዉ የማይችሏቸዉን አካላትን ጭምር አካተዉ አዲስ ክስ ማቅረባቸዉ ሕግን የጣሰ ነዉ ሊባል የሚቻል አይደለም። ከዚህም ባሻገር በፍ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 234(1)(ረ) ላይ እንደተደነገገዉ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ማቅረብ ለተከሳሹ ምርጫ የተተወ እንጂ አስገዳጅነት ያለዉ አይደለም። በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በዚህ ረገድ የሰጠዉ ዉሳኔም ሕግን መሠረት ያደረገ ሆኖ አልተገኘም።

በሌላ በኩል የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ወደ ፍሬ ነገሩ ክርክር ዉስጥ በመግባት በጉዳዩ ላይ 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡትን ይግባኝንም ሆነ አመልካች ያቀረቡትን የመስቀልኛ

ይግባኝን አልተመለከተዉም፡፡ በመሆኑም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ወዳልታየዉ የፍሬ ነገር ክርክር ዉስጥ ገብቶ ዉሳኔ ሊሰጥ አይችልም፡፡ ስለሆነም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ዉሳኔ ከላይ በዝርዝር የተመለከቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተቶች የተፈጸሙበት ሆኖ ስለተገኘ ስህተቶቹን በማረም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ዉሳኔ**

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 224054 ጥር 30 ቀን 2016 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9 (1)(ለ) መሠረት በሙሉ ድምጽ ተሽሯል፡፡

2. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ወደ ፍሬ ነገሩ ክርክር በመግባት 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡትን ይግባኝና አመልካች ያቀረቡትን የመስቀልኛ ይግባኝ መርምሮ የመሰለዉን ዉሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩ በፍ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 343(1) መሠረት እንዲመለስለት ተወስኗል፡፡

3. የዚህን ሰበር ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡ በዚህ የሰበር ክርክር ምክንያት የተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ ካለ እንዲነሳ ታዟል፤ ይጻፍ፡፡ መዝገቡ በዉሳኔ ስለተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 262505

የካቲት 26 ቀን 2017ዓ/ም

ዳኞች ፡-ገበየሁ ፈለቀ

አለማየሁ ሹናራ

ደረጀ አያና

ኑረዲን ከድር

ብርሃኑ መንግስቱ

አመልካች፡- ተወልደ ግደይ የኤሌክትሪክ ኬብል እና ዋየር ፋብሪካ፡-

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፡- ነገረ ፈጅ ሄኖክ ከበደ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ ለቅድመ ጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓትን የሚመለከት ነው፡፡ጉዳዩ የተጀመረው በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካች አቤቱታ አቅራብነት ነው፡፡በአመልካች የቀረበው አቤቱታ ይዘትም በአጭሩ ከተጠሪ ጋር ግንቦት 22 ቀን 2003 ዓ.ም እና ነሀሴ 28 ቀን 2011 በተደረገ የብድር አከፋፈል ስምምነት ብር 692,389,514.50 የብድር ገንዘብ ያለበት መሆኑን፤ብድሩ ተከፍሎ የሚያልቀው የካቲት 27 ቀን 2016 ዓ.ም መሆኑን፤ከዚህ ውሰጥ ብር 419,224,378.70 መክፈሉን፤ ባጋጠመው የውጭ ምንዛሪ እጥረት ምክንያት የፋይናንስ እጥረት ያጋጠመው ቢሆንም አሁን የፋይናንስ እጥረት መሰረት የሆነው የጥሬ እቃ አቅርቦት ችግር በመፈታቱ የፋይናንስ ችግሩ በቅርብ የሚቀረፍ መሆኑን እና ይህም በሚዋቀርለት የዕዳ መክፈያ ጊዜ ውስጥ በተጨባጭ ዕዳውን መክፈል የሚያስችለው መሆኑን እንደዚሁም ሌሎች ምክንያቶችን በመዘርዘር ለቅድመ ጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ

ሥርዓት ተፈቅዶለት ዕዳው ተዋቅሮ የሚከፍልበት ጊዜ እንዲሰጠው፣ዕዳው ሊከፈል የሚችልበትን አማራጭ መፍትሄዎች የሚያጠና ለፍ/ቤቱ፣ለአመልካች እና ለተጠሪ እንዲሁም ሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች ድጋፍ የሚያደርግ እና ሪፖርት የሚያቀርብ ባለሙያ እንዲሾም ጠይቀዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤትም በአመልካች የቀረበውን አቤቱታ እና ማስረጃ በመመርመር በሰጠው ውሳኔ አመልካች አጋጥሞኛል ላለው የፋይናንስ እጥረት እንደ መፍትሄ አድርጎ ያቀረባቸው ጉዳዮች ለዕዳ ክፍያ መዋል የሚችል ገንዘብ የሚያገኝበት እድል መኖሩን አመላካች መሆኑን፣የአመልካች አቅም እና የዕዳ ክፍያ ማሳያዎች አመልካች ድርጅት አሁን ከገጠመው መለስተኛ ገንዘብ ችግር መደበኛ ስራውን እያከናወነ ከገንዘብ ጠያቂዎቹ ጋር በባለሙያ ድጋፍ ዕዳውን እንዲያዋቅር እድል ቢሰጠው ዕዳውን ያለመክፈል ሁኔታው ከመባባስ እንደሚያገግም መገንዘቡን ጠቅሶ በንግድ ህጉ አንቀጽ 617 መሰረት ለቅድመ ጥንቃቄ ዕዳን መልሶ ማዋቀር ሥነ ሥርዓት ሊከፈት ይገባል በማለት ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዘርፍ ባለሙያ እንዲሾም እና የተሾመው ባለሙያ መልሶ የማዋቀሩን እቅዱን በህጉ መሰረት በማዘጋጀት ለፍ/ቤቱ በአራት ወራት ውስጥ እንዲያቀርብ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

የአሁን ተጠሪ የሥር ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 245314 የሰጠውን የዕግድ ትዕዛዝ እና በመ/ቁጥር 488935 ደግሞ የዕዳ ማዋቀር ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም የይግባኝ አቤቱታውን ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡የይግባኝ አቤቱታው የቀረበለት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም አመልካች መልስ እንዲሰጥበት በማድረግ በሰጠው ውሳኔ የአሁን አመልካች የዕዳ መልሶ ማዋቀር ሥነ ሥርዓት እንዲከፈትለት አቤቱታ ሲያቀርብ ተጠሪን በመልስ ሰጪነት የጠቀሰው መሆኑን፣ተጠሪም በቀጠሮው ቀን እየቀረበ ክርክሩን ሲከታተል እና በዕግድ አቤቱታው ላይ አስተያየት የሰጠ ቢሆንም በዕዳ መልሶ ማዋቀር አቤቱታ ላይ መልስ ወይም አስተያየት እንዲያቀርብ አለመደረጉንና የፍትሐብሄር ክርክር በፍትሐ ብሄር ሥነ ሥርዓት ህጉ መሰረት የሚመራ እንደመሆኑ አንድ አቤቱታ ወይም ክስ ሲቀርብ ለቀረበው ክስ ወይም አቤቱታ ተከሳሽ ወይም ተጠሪ የሆነ ተከራካሪ የመከላከያ መልሱን የማቅረብ መብት እንዳለው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 232 ስር መመልከቱን፣በንግድ ህጉ አንቀጽ 598 መሰረት ገንዘብ ጠያቂዎች ዕዳን መልሶ በማዋቀር ሥነ ሥርዓት ወቅት በአጠቃላይ አስተያየት የማቅረብ እና የመሰማት መብት ያላቸው መሆኑን፣እንዲሁም በአንቀጽ 617 ላይ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት ለመፍቀድ መሟላት የሚገባቸው ሁኔታዎች ያሟሉ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት እና ውሳኔ ላይ ለመድረስ ባለገንዘቦች መልስ ወይም አስተያየት እንዲሰጡ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን የሚያመላክት መሆኑን በመጥቀስ የስር ፍ/ቤት በአመልካች የቀረበለትን የዕዳን መልሶ የማዋቀር ጥያቄ ተጠሪ በመልስ ሰጪነት ተመዝግቦ ሳለ የተጠሪን መልስ ወይም አስተያየት ሳይቀበል ውሳኔ ላይ መድረሱ ከላይ የተጠቀሱትን ድንጋጌዎች የሚጥስ ነው በማለት የስር ፍ/ቤት የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ በአመልካች የቀረበውን የዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓት

ይከፈትልኝ አቤቱታ ላይ ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ በማድረግ የመሰለውን እንዲወስን ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 343(1) መሰረት ወደ ስር ፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መልሶታል፡፡የአመልካች ድርጅት በተጠሪ እንዳይሸጥ መታገዱን በተመለከተ አመልካች ያቀረበው የዕዳን መልሶ የማወቀር አቤቱታ ውጤት ሳይታወቅ የአመልካች ድርጅት በሀራጅ እንዲሸጥ የሚደረግ ከሆነ የአመልካችን ዕዳን የማዋቀር አቤቱታ መብት የሚያጣብብ፣አመልካች ዕዳን የማዋቀር ዕድል ተሰጥቶት ዕዳውን መክፈል የሚችልበትን ዕድል የሚያሳጣ እና ተያያዥ ጉዳቶች የሚያደርስ መሆኑን በመግለጽ የሥር ፍ/ቤቱ እግድ መስጠቱ የሚነቀፍ አይደለም በሚል ወስኗል፡፡

የአሁን ሰበር አቤቱታ የቀረበውም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት ለማስለወጥ ነው፡፡በአመልካች የቀረበው ሰበር ቅሬታውም በአጭሩ አመልካች ለስር ፍ/ቤት አቤቱታ ያቀረበው በንግድ ሕጉ 3ኛ መፅሐፍ ስር የተጠቀሱትን ሶስት ሥነ ሥርዓቶች ውስጥ አንዱ የሆነውን ለጥንቃቄን ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓት እንዲከፈትለት ነው፡፡ይህ የንግድ ህግ ክፍል የሚመራው እና የሚፈፀመው በዚህ በልዩ ሁኔታ በንግድ ሕጉ ላይ የተቀመጠውን ሥነ ሥርዓት መሰረት በማድረግ ነው፡፡ይህንን የንግድ ሕጉን መሰረት ያደረገ አቤቱታ ለፍ/ቤት ሲቀርብ ፍ/ቤቱ አቤቱታውን መምራት፣ማስተዳደር ብሎም ውሳኔ መስጠት ያለበት በልዩ ሁኔታ በንግድ ሕጉ የተቀመጠውን ሥነ ሥርዓት በመከተል ሊሆን ይገባል፡፡በመሆኑም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ጉዳዩ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ህጉ ላይ በተቀመጠው መደበኛ የክርክር አመራር ነው መታየት ያለበት፣ተጠሪም መልስ ሰጥቶ ክርክር መደረግ አለበት በማለት የሰጠው ውሳኔ የንግድ ሕጉን የሚቃረን ነው፡፡ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት ለፍ/ቤት አቤቱታ ሲቀርብ አመልካቹ በዚህ አቤቱታ ላይ መግለፅ እና ማካተት ያለበት ጉዳይ ምን ምን እንደሆነ፣ በምን ያህል ጊዜ ውስጥ አቤቱታው ለፍ/ቤት መቅረብ እንዳለበት በን/ህ/ቁ 617 ስር ተመልክቷል፡፡በዚህ መልኩ አቤቱታ ከቀረበ በኋላ ፍ/ቤቱ አቤቱታውን ተመልክቶ ራሱ ከሕጉ አንፃር መርምሮ ሥነ ሥርዓቱ ሊከፈት ይገባል ወይስ አይገባም በሚለው ጉዳይ ላይ ውሳኔ እንደሚሰጥ በን/ህ/ቁ 618 ስር ተመልክቷል፡፡ከዚህ ውጪ ፍ/ቤቱ ሥነ ሥርዓቱ እንዲከፈት ውሳኔ ለመስጠት ባለገንዘቦቹን ጠርቶ ክርክራቸውን መስማት እንዳለበት በሕጉ ላይ አልተመለከተም፡፡ባለገንዘቦች የሚጠሩት ፍ/ቤቱ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት ውሳኔ ከተሰጠ በኃላ ሲሆን በዚህም ጊዜ የሚጠሩት በፍ/ቤት ሳይሆን ዕዳን መልሶ ማዋቀር ሥራ እንዲሰራ በሚመደበው ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዘርፍ ባለሙያ ስለመሆኑ በን/ህ/ቁ 621 ስር ተመልክቷል፡፡የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይህንን ግልፅ የሆነ ድንጋጌ በሚቃረን መልኩ ዕዳን ለቅድመ ጥንቃቄ  መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት ለፍ/ቤት አቤቱታ ሲቀርብ ሁሉም ገንዘብ ጠያቂዎች ቀርበው መልስ መስጠት አለባቸው በሚል ከን/ህ/ቁ 598 በሚቃረን መልኩ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

ይህ ችሎትም የአመልካችን አቤቱታ መርምሮ አመልካች በስር ፍ/ቤት ያቀረበው ክስ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥርዓትን የሚመለከት ከመሆኑ አኳያ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የስር ፍ/ቤት ተጠሪ በጉዳዩ ላይ መልስ እንዲሰጥ በማድረግ የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ እንዲወስን በማለት የወሰነበትን አግባብ ዕዳን መልሶ ለማዋቀር በሚመለከት ከተደነገጉት የንግድ ህጉ አንቀጽ 588 እና ተከታታይ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ሊመረመር የሚገባው ነው በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡

ተጠሪም ለቀረበው የሰበር አቤቱታ የሰጠው መልስ  የንግድ ህጉ አንቀጽ 588 ዓላማ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ እና ጊዜውን ጠብቆ በሚከናወን ሥነ ሥርዓት አማካኝነት የፋይናንስ ችግር ውስጥ ያሉ ተበዳሪዎችን መልሰው እንዲዋቀሩ እና ስራ እንዲቀጥሉ ማስቻል ብቻ ሳይሆን የገንዘብ ጠያቂዎችን ጥቅምም ማስጠበቅ እንደሚኖርበት የሚደነግግ በመሆኑ አመልካች ጉዳዩ በመደበኛ የሙግት ሥርዓት የሚካሄድበት አግባብ የለም በማለት ያቀረበው አቤቱታ ተገቢነት የለውም፡፡ _ አመልካች የዕዳ ይዋቀርልኝ አቤቱታውን ለፍርድ ቤት ሲያቀርብ ያቀረባቸው ሰነዶች በንግድ ህጉ ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶች ስለማሟላታቸው ማረጋገጥ የሚቻለው አበዳሪዎች (ገንዘብ ጠያቂዎች) በቀረበው ሰነድ ላይ ያላቸውን አስተያየት ሲሰጡ መሆኑን፤የንግድ ህጉ አንቀፅ 597(1) ማንኛውም የዕዳ ማወቀር ሥነ ሥርዓት በሚከናወንበት ወቅት የባለዕዳውን/ተበዳሪውን ሥራ የማስቀጠል ብቻ ሳይሆን የገንዘብ ጠያቂዎችን ትክክል ጥቅም ማስጠበቅ እንደሚኖርበት በአስገዳጅነት ያስቀመጠ መሆኑን፤ይህ ሊሆን የሚችለው ደግሞ ፍርድ ቤቱ አመልካች በራሱ በሚያቀርበው ሰነድ እና አቤቱታ ላይ ብቻ መሰረት በማድረግ ሳይሆን በሚቀርበው አቤቱታ መሰረት ገንዘብ ጠያቂዎች ጥቅማቸውን የሚነካ ጉዳይ እና በህጉ ላይ የተቀመጡትን አስገዳጅ ድንጋጌዎችን የሚያሟሉ ስለመሆናቸው ለፍርድ ቤቱ እንዲያቀርቡ በማድረግ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን በመመርመር የመልሶ ዕዳን ማወቀር ውሳኔ የሚሰጥበት መሆኑን፤ባለገንዘቦች የሚጠሩት ፍ/ቤቱ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ ከሆነ ገንዘብ ጠያቂዎች ስለገንዘብ ክፍፍል እንጂ የዕዳ መልሶ ማዋቀሩ ጥቅማቸውን እንደሚነካ እና የቀረበውም አቤቱታ ህጉን ተከትሎ ስለመሆኑ ማረጋገጥ የማይችሉበት መሆኑን፤በዚህም መሰረት አመልካች ያቀረበው አቤቱታ ተገቢነት የሌለው በመሆኑ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በሚል ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም ተጠሪ በሰጠው መልስ ላይ ነሐሴ 16 ቀን 2016 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀውን የሚመስል ሲሆን ከላይ የተያዘዉን ጭብጥ መሠረት በማድረግ በስር ፍርድ ቤት በተሰጠው ውሳኔ ላይ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የሕግ ስህተት መፈጸም አለመፈጸሙን አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡እንደመረመርነውም አመልካች ተጠሪን በመሰየም ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓት እንዲከፈትልኝ የሚል ዳኝነት በመጠየቅ ምክንያቱንም ጭምር በመዘርዘር ለፌዴራል ከፍተኛ

ፍርድ አመልክቷል፡፡ተጠሪ በክርክሩ ለአመልካች ገንዘብ በማበደር የተጠሪን ፋብሪካ ለሰጠዉ ብድር መያዣ ያደረገ መሆኑን በፋብሪካዉ ላይ የተሰጠዉ እግድ እንዲነሳለት ሲያመለክት ከመግለጽ ዉጭ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓት ለማስከፈት ባቀረበ አቤቱታ ላይ ክርክር እንዲያሰማ አልተደረገም፡፡ተጠሪ ብድር በሰጠው ንብረት ላይ በስር ፍርድ ቤት ስለተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ አስተያየቱን የሰጠ ቢሆንም በቀረበው የዕዳ መልሶ ማዋቀር አቤቱታ ላይ አስተያየት ያልሰጠ ስለመሆኑ ከስር ፍርድ ቤት ክርክር መረዳት የሚቻል ነው፡፡ፍርድ ቤቱም በአመልካች የቀረበውን ዕዳን መልሶ የማዋቀር አቤቱታ በመመርመር ያጋጠመውን መለስተኛ የገንዘብ ችግር መደበኛውን የንግድ ስራ እያከናወነ ከገንዘብ ጠያቂዎቹ ጋር በባለሙያ ድጋፍ ዕዳውን እንዲያዋቅር ዕድል ቢሰጠው ዕዳውን ያለመክፈል ሁኔታው እየተባበሰ እንዳይቀጥል ያደርጋል በሚል የቀረበውን ለቅድመ ጥንቃቄ ዕዳን የማዋቀር ሥነ ስርዓት እንዲከፈትና ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዕቅዱ በህጉ መሠረት ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ ወስኗል፡፡

ተጠሪ የዕግድ ትዕዛዝ አይነሳም በመባሉ እና በተሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታውን ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ የዕዳን መልሶ የማዋቀር፣የማደራጀት እና የመክሰር ዓላማዎችን ለማሳካት እንዲረዳ ዕዳን መልሶ የማዋቀር አቤቱታ ውጤት እስኪታወቅ ድረስ የባለዕዳው ንብረት ለዕዳው መክፈያ እንዳይሸጥ መታገዱ በአግባቡ ነው፣ ፍርድ ቤቱ ለቅድመ ጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር አቤቱታ ሲቀርብለት በንግድ ህግ አንቀጽ 617(1) መሠረት የቀረበው አቤቱታ በድንጋጌው ስር የተመለከቱትን ሁኔታዎች ያሟላ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት እና ውሳኔ ላይ ለመድረስ አመልካች በአቤቱታው ላይ አስተያየት ሳይሰጥ ዕዳው እንዲዋቀር ዕቅድ ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ መወሰኑ ከህጉ አግባብ ውጪ ነው በሚል የተሰጠውን ውሳኔ በመሻር ተጠሪ በቀረበው የዕዳን መልሶ መዋቀር አቤቱታ ላይ መልስ እንዲሰጥበት በማድረግ መርምሮ እንዲወስን ወደ ስር ፍርድ ቤት የመለሰ ስለመሆኑ የሚያስገነዝብ ነው፡፡

በመሆኑም ለቅድመ ጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር አቤቱታ ለፍርድ ቤት ሲቀርብ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓት ከመከፈቱ በፊት ገንዘብ ጠያቂዎች በአቤቱታው ላይ በተጠሪነት የመሰማት መብት አላቸዉ ወይስ የላቸዉም? የመሰማት መብት አላቸዉ የሚባል ከሆነ ከጉዳዩ ባህሪይ አንጻር የመሰማት መብት አድማስ እና ክርክሩ በምን አግባብ ሊመራ ይገባል? የሚሉ ነጥቦች የዚህን ችሎት ዉሳኔ የሚሹ ናቸዉ፡፡

የንግድ ህግ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 እንደ አዲስ ካካተታቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ ለቅድመ ጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓት በተመለከተ በንግድ ህግ አንቀጽ 588 እና ተከታዮቹ አንቀጾች ስር ያሉ ጠቅላላ ድንጋጌዎች እንዲሁም በአንቀጽ 617 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች የተመለከተዉ ነው፡፡<u>ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓት ዓላማው የሚመለከታቸው ገንዘብ</u>

ጠያቂዎች በሙሉ ድምጽ የሚፈቅዱ ከሆነ በፍርድ ቤት በሚጸድቅ ዕቅድ መሠረት የፋይናንስ ችግር ውስጥ ያሉ ተስፋ የሚጣልባቸው ተበዳሪዎች ውልን መሰረት ባደረገ መልኩ በጊዜ ዕዳቸውን ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ መልሰው እንዲያዋቅሩ እና ሥራቸውን እንዲቀጥሉ ወይም የንግድ ሥራ እንቅስቃሴው በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ የንግድ ሥራ ለመሸጥ መዘጋጀት እንዲችሉ ማድረግ ስለመሆኑ የንግድ ህግ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 588(2) እና 629 ስር ተደንግጎ የሚገኝ ነው፡፡

ለቅድመ ጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓት ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት የሚከፈተው ክፍያዎችን ገና ያላቋረጠ ወይም ክፍያዎችን ካቋረጠ አርባ አምስት ቀናት ያልሞላው እና የኢኮኖሚ ወይም የፋይናንስ ችግር በተጨባጭ ያጋጠመው ወይም ያጋጥመዋል ተብሎ የሚጠበቅ ባለዕዳ ሲያመለክት ብቻ ስለመሆኑ በንግድ ህጉ አንቀጽ 617(1) ስር ተመልክቷል፡፡ ፍርድ ቤትም በዚህ ድንጋጌ የተደነገጉ መሠረታዊ ቅድመ ሁኔታዎች ወይም ለቅድመ ጥንቃቄ ዕዳን መልሶ ለማዋቀር የሚያስችል ህጋዊ መመዘኛ ስለመሟላት አለመሟላቱ በመመርመር የወደፊት ሂደቱ ላይ ውሳኔ የሚሰጥ ነው፡፡ከዚህ አንፃር ለቅድመ ጥንቃቄ ዕዳ መልሶ እንዲዋቀር በሚቀርብ አቤቱታ ላይ ሥነ ሥርዓቱ እንዲከፈት ከመታዘዙ በፊት ገንዘብ ጠያቂዎች በሂደቱ ተካፋይ የሚሆኑበት አግባብ በህጉ ላይ ያልተገለጸ ቢሆንም ከባለገንዘቦች የመሰማት መብት እንዲሁም በሕጉ አንቀጽ 588(1) ስር ሥነ ሥርዓቱ ቀልጣፋ እና ዉጤታማ በሆነ እና ጊዜዉን ጠብቆ በሚከናወን ሥነ ሥርዓት አማካኝነት የኢኮኖሚ መረጋጋትን ማስፋፋት፣ የንብረቱን ዋጋ ከፍ ማድረግ እና የሕግ ተገማችነትንና ግልጽነትን ማረጋገጥ የሚሉ ዓላማዎችን ባገናዘበ አኳኋን መታየት ይኖርበታል፡፡

ከላይ እንደተገለጸዉ ለቅድመ ጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓት ከመከፈቱ በፊት በንግድ ህጉ አንቀጽ 617(1) ሥር የተደነገጉት መሠረታዊ ቅድመ ሁኔታዎች (substantive pre-conditions መሟላታቸዉን ማረጋገጥ የሚገባ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በሕጉ አንቀጽ 588/1 መሠረት ለቅድመ ጥንቃቄ ዕዳን መልሶ ከማዋቀር ሥነ ሥርዓት አከፋፈት ጋር የተያያዘዉ የፍርድ ሂደት ቀልጣፋ፣ ዉጤታማ እና ግልጽ በሆነ አግባብ መከናወን ይኖርበታል፡፡በዚህ መሠረት ለቅድመ ጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት ከመታዘዙ በፊት ገንዘብ ጠያቂዎች በሂደቱ ተከፋይ እንዲሆኑና በተለይም በንግድ ሕጉ አንቀጽ 588/1 እና 617/1 ስር የተደነገጉት መሠረታዊ ዓላማዎች ሊሳኩ የሚችሉበት ሁኔታ እና ቅድመ ሁኔታዎቹ መኖር አለመኖራቸዉን እንዲያስረዱ በማድረግ የፍርድ ሂደቱ ዉጤታማ እና ግልጽ እንዲሆን ማድረግ ይገባል፡፡
እንዲሁም በንግድ ሕጉ አንቀጽ 598 ስር በተደነገገዉ መሰረት ለቅድመ ጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓት ከመከፈቱ በፊት በሚኖረዉ የፍርድ ሂደት ጭምር የገንዘብ ጠያቂዎችን ተሳትፎ (participation) እና የመሰማት መብት ማረጋገጥ ይገባል፡፡እነዚህን መብቶች ማረጋገጥ

ከአመልካቹም ሆነ ከገንዘብ ጠያቂዎቹ አንጻር የንብረቱን ዋጋ ከፍ ከማድረግ፤ የኢኮኖሚ መረጋጋት ከማስፋፋት፣ተስፋ የሚጣልባቸዉ ተበዳሪዎች ብቻ በሥነ ሥርዓቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከማድረግ ባለፈ ተስፋ የማይጣልባቸዉ ተበዳሪዎች ሥነ ሥርዓቱን በማስከፈት ገንዘብ ጠያቂዎችን ለአላስፈላጊ ኪሳራ እንዳይዳርጉ፣የፍርድ ቤቱን እና በሂደቱ ተካፋይ የሚሆኑ አካላትን የጊዜ፣የቁስና የገንዘብ ሀብት እንዳያባክኑ ያደርጋል፡፡

ከዚህ አንፃር በተያዘው ጉዳይ አመልካች ከተጠሪ ለተበደረው ገንዘብ ለጥንቃቄ ዕዳ መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓት ለስር ፍርድ ቤት ሲያቀርብ ተጠሪ በመሰየም ተጠሪን ጨምሮ ከሶስት የተለያዩ ባንኮች የተለያየ መጠን ያላቸውን ገንዘብ እንደተበደረ፣የሌሎች ሁለቱ ባንኮች ብድር በተመለከተ ክፍያ እንደላቀመ፣ከተጠሪ ከተበደረው ገንዘብ ውስጥ 37.5% የሚሸፍነውን ክፍያ እንደፈጸመ፣ተጠሪ ማስጠንቀቂያ ከሰጠው በኋላ ብር 100,000 ክፍያ መፈጸሙን፣የፋይናንስ ችግር ያጋጠመውን ችግሩ የሚፈታበት አስቻይ ሁኔታ የተፈጠረ መሆኑን በመጥቀስ ዕዳው ቢዋቀርለት ስራውን እየሰራ ዕዳውን በአጭር ጊዜ ውስጥ ለመክፈል የሚያስችለው ስለሆነ ዕዳው እንዲዋቀርለት አቤቱታውን ያቀረበ ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት መዝገብ የሚያሳይ ነው፡፡አመልካች የአሁኑን ተጠሪ በተጠሪነት በመሰየም አቤቱታውን አቅርቦ እያለ ፍርድ ቤቱ ከላይ በአመልካች በተጠቀሱት ምክንያቶች ላይ ተጠሪ አስተያየቱን በቃል ወይም በጽሁፍ በሂደቱ ላይ ተጽዕኖ በማይፈጥር ሁኔታ ሳይሰማ ዕዳውን የማዋቀር ዕቅድ ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ የወሰነበት አግባብ ወደፊት ባሉት ሂደቶች ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል ከመሆኑም በላይ የተጠሪን የመሰማት መብት ከግምት ባለማስገባት የተሰጠው ውሳኔ ውስጥ የተከራካሪ ወገኖችን በእኩልነት የመዳኘት መብትን ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም የሚገባ ነው፡፡ በሌላም በኩል አዲሱ የንግድ ህግ ለቅድመ ጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር የሥነ ሥርዓት የቆይታ ጊዜ በሚመለከት ለቅድመ ጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዕቅዱ ከሚመለከታቸዉ ገንዘብ ጠያቂዎች ጋር በአራት ወራት ዉስጥ ሊጠናቀቅ እንደሚገባ፣በሚመለከታቸዉ ገንዘብ ጠያቂዎች በሙሉ ድምፅ ተቀባይነት ስለማግኘቱ ባለዕዳው ካስረዳ ፍርድ ቤቱ ጊዜዉ እንዲራዘም ሊፈቅድ እንደሚችልና ማራዘሚያዎችን እና እድሳቶችን ጨምሮ ዕቅዱ የሚጠናቀቅበት አጠቃላይ ጊዜ ከ8 ወራት መብለጥ የለሌበት ስለመሆኑ በንግድ በሕግ አንቀጽ 618 ስር ተመልክቷል፡፡ይህም የሚያሳየን ሥነ ሥርዓቱ ተጀምሮ መጠናቀቅ ያለበት በሕጉ በተቀመጠዉ አጭር ጊዜ ዉስጥ ሊሆን እንደሚገባ ሲሆን ለቅድመ ጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓት ሂደት ውስጥ ተካፋይ የመሆኑ ገንዘብ ጠያቂዎች በአብዛኛዉ ባንኮች፣ አበዳሪ ተቋማት እና ሌሎች የንግድ ድርጅቶች ወይም ነጋዴዎች ስለሚሆኑ የገንዘብ ጠያቂዎችን ተሳትፎና የመሰማት መብት ለማረጋገጥ ሲባል ብድሩ እንዳይበላሽ፣የብድር ወለዱ እየጨመረ ሄዶ የተበዳሪዉ ግዴታ እንዳይከብድ፣ኢኮኖሚ ከማረጋጋት ጋር እና በንብረት ዋጋ ላይ አሉታዊ ዉጤት እንዳይከተል ለቅድመ ጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ-ሥርዓት ሊመራ የሚገባዉ በህጉ የተዘረጋውን ሥርዓት

በተከተለና ዓላማዉን ከግብ ሊያደርስ በሚችል መልኩ በልዩ ሁኔታ ቀልጣፋ ሂደት በመከተል ሊሆን ይገባል፡፡በመሆኑም ሥነ-ሥርዓቱ መደበኛውን የፍትሐ ብሔር ክስ ክርክር አመራር ሥነ ሥርዓት ተከትሎ ተከሳሽ ወይም ገንዘብ ጠያቂዎች መከላከያ መልስ አቅርበዉ፣ክስ ተሰምቶ፣አከራካሪ ጭብጥ ተይዞ፣የፍሬ ነገር ጭብጥ በማስረጃ ተረጋግጦ ዉሳኔ ሊያገኝ ይገባል የሚባል አይደለም፡፡

ከላይ ከተገለጸዉ አንጻር የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ክርክሩን የመሩበትን አግባብ እና የሰጡትን ዉሳኔ ስንመለከት ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁኑን ተጠሪ በተጠሪነት ከመሰየም ባለፈ ሥነ ሥርዓቱ እንዲከፈት ከመታዘዙ በፊት በሂደቱ እንዲሳተፍ አለማድረጉ እና ሥነ ሥርዓቱ እንዲከፈት የሚያደርጉ መሠረታዊ ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት አለመሟላታቸዉን በተመለከተ ተጠሪ የመሰማት መብቱን እንዲጠቀም ሳያደርግ ሥነ ሥርዓቱ እንዲከፈት ማዘዙ፤የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም የጉዳዩን ልዮ ባህሪይ በግምት ውስጥ ሳያስገባ በስር ፍርድ ቤት ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓት እንዲከፈት የተሰጠውን ውሳኔ በመሻር አመልካች ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለቅድመ ጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ-ሥርዓት እንዲከፈት ዳኝነት በመጠየቅ ባቀረበዉ አቤቱታ ላይ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ በማድረግ የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ ተገቢውን እንዲወስን በሚል ክርክሩ በመደበኛ ሥነ ሥርዓት እንዲመራ የተሰጠው ውሳኔ የንግድ ህጉ ለቅድመ ጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓት በግልጸኝነት፣በቅልጥፍና እና በዉጤታማነት መመራት አለበት በሚል የደነገገዉን ዓላማ ያላገናዘበ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ሲጠቃለል ለቅድመ ጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓት የሚመለከት ዳኝነት በሚታይበት የፍርድ ሂደት ዉስጥ ተስፋ የሚጣልባቸዉ ተበዳሪዎች ብቻ በሥነ ሥርዓቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያደርግና የገንዘብ ጠያቂዎችን ትክክለኛ ጥቅም የሚያስጠብቅ መርሆዎች መከተል ይገባል(የሕጉ አንቀጽ 597/1 ይመለከቷል)፡፡ሥነ ሥርዓቱ እንዲከፈት የቀረበዉን አቤቱታ ከመቀበል ጀምሮ የሚኖረዉን የፍርድ ሂደት ግልጽ፣ቀልጣፋ እና ዉጤታማ ማድረግ ይገባል፡፡እነዚህን መርሆዎች ተግባራዊ ማድረግ እንዲቻል፤ለቅድመ ጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ-ሥርዓት እንዲከፈት ዳኝነት ተጠይቆ የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት አግኝቶ ሥነ ሥርዓቱ ከመከፈቱ በፊት በንግድ ሕጉ አንቀጽ 588/1 የተደነገጉትን ዓላማዎች ከማሳካት እና በሕጉ አንቀጽ 617/1 ስር የተደነገጉት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት አለመሟላታቸዉን በሚገባ ለማረጋገጥ በሚያስችል ሁኔታ ጉዳዩን ተገንዝቦ ለቅድመ ጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓት ሊከፈት የሚገባ መሆን አለመሆኑ ላይ ትክክለኛ ዉሳኔ መስጠት በሚያስችል ደረጃ ብቻ ገንዘብ ጠያቂዎች በቃል ወይም በጽሁፍ አስተያየታቸዉን በማስረጃ አስደግፈዉ እንዲያቀርቡ በመፍቀድ በፍርድ ሂደቱ ተሳታፊ እንዲሆኑና የመሠማት መብታቸዉን እንዲጠቀሙ መፍቀድ ይገባል፡፡የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ለቅድመ ጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ-ሥርዓት እንዲከፈት በአመልካች በቀረበው አቤቱታ ላይ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር በመደበኛ በሚመስል ሥነ-ሥርዓት ተሰምቶ እንዲወሰን ጉዳዩን ለስር ፍርድ ቤት በመመለስ የተሰጠውን ውሳኔም ሆነ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካች በቀረበው አቤቱታ ላይ ተጠሪን ሳይሰማና ሳያሳትፍ ሥነ-ሥርዓቱ እንዲከፈትና ዕዳን መልሶ የማዋቀር ዕቅድ ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ የወሰነበት አግባብ በንግድ ሕጉ 3ኛ መጽሐፍ የተደነገጉትን መርሆዎችና የሥነ-ሥርዓቱን ዓላማዎች ያላገናዘቡ ዉሳኔዎች ስለሆኑ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ለ) እና 10(1/ለ) መሠረት ሊታረሙ የሚገባቸዉ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ናቸዉ፡፡በመሆኑም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 24534/248935 ላይ 17 ቀን 2016 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 300872 ሰኔ 08 ቀን 2015 ዓ.ም  የሰጠው ውሳኔ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1)(ለ) መሰረት ተሻሽለዋል፡፡

2. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ  በንግድ ሕጉ አንቀጽ 588/1 የተደነገጉትን ዓላማዎች ከማሳካት እና በሕጉ አንቀጽ 617/1 ስር የተደነገጉት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት አለመሟላታቸዉን በሚገባ ለማረጋገጥ በሚያስችል ሁኔታ ነገሩን ተገንዘቦ ለቅድመ ጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓት ሊከፈት የሚገባ መሆን አለመሆኑ ላይ ትክክለኛ ዉሳኔ መስጠት በሚያስችል ደረጃ ብቻ ገንዘብ ጠያቂዎች በቃል ወይም በጽሁፍ አስተያየታቸዉን በማስረጃ አስደግፈዉ እንዲያቀርቡ በማድረግ እንደአስፈላጊነቱ ፍርድ ቤቱ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 617/2 መሠረት ተጨማሪ ማስረጃ አስቀርቦ በመመርመር ሕግን መሠረት ያደረገ ዉሳኔ እንዲሰጥ በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(2) መሰረት ተመልሶለታል፡፡

3. በዚህ ችሎት ደረጃ የወጣ ወጭ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ተወስኗል፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፣ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ በአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 263727

ቀን ፡- የካቲት 25 ቀን 2017 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች ፡- ብርሃን ባንክ አ/ማ - ነ/ፈጅ ጌቱ ስጦታው ቀረበ

ተጠሪ ፡- ብርሃን ባንክ መሠረታዊ የሠራተኞች ማሕበር - ፕሬዝዳንት ኑሪ አማን ቀረቡ

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ።

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው። የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች የስር ተከሳሽ ሲሆን ተጠሪ ከሳሽ ነበር። ተጠሪ ሐምሌ 26 ቀን 2015 ዓ/ም ጽፎ ባቀረበው ክስ አመልካች ድርጅት ለሁሉም ሰራተኞች በሚል በተጻፈ ጥቅማጥቅም የተወሰነ መሆኑ ተገልጾ እያለ የቤት አበል በተለምዶ በጽሕፈት መደብ ላይ ያልሆኑ /non-clericals/ የሚሰሩ ሰራተኞች አልከፍልም ማለቱ የእኩልነት መብት የሚጥስ በመሆኑ የቤት አበል እንዲከፈል እንዲወሰን ዳኝነት ጠይቋል። አመልካች በሠጠው መልስ ደብዳቤው ለሁሉም ሠራተኞች በሚል የተጻፈው የተለያየ የጥቅማጥቅም ሁኔታዎች የተካተቱበት ስለሆነ ነው፣ በጽሕፈት መደብ ላይ ላልሆኑ ሰራተኞች የቤት አበል ጥቅማጥቅም

አልተወሰነም፣ ጥቅማጥቅም ሳይወሰን ክፍያ እንዲፈጸም ዳኝነት ሊጠየቅበት አይችልም፣ በተመሳሳይ የሥራ መደብ ላይ ለሚሰራ ሠራተኞች የተለያየ ጥቅማጥቅም እንዲያገኙ ያልተወሰነ በመሆኑ የእኩልነት መብትን አልተጣሰም፣ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ግራቀኙን አከራክሮ ተጠሪ ቀደም ሲል ክሱን ለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ አቅርቦ ሥልጣን የለኝም በማለት ክሱን የሰረዘ ሲሆን በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔው ጸንቷል፡፡ ይሕ ውሳኔ ያልተሻረ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለመመልከት ሥልጣን አለው፡፡ ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ በጽሕፈት መደብ ላይ ያልሆኑ ሠራተኞች የቤት አበል እንዲከፈላቸው በአመልካች ድርጅት አልተወሰነም፣ የተለያየ የሥራ መደብ ላይ የሚሰሩ ሠራተኞች የተለያየ የጥቅማጥቅም መብት መወሰኑ የእኩልነት መብት የሚጥስ አይደለም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በበኩሉ የቤት አበል የተወሰነው የኑሮ ውድነትን ታሳቢ ያደረገ መሆኑ ከሰነዱ መረዳት ስለሚቻል በጽሕፈት መደብ ላይ ያልሆኑ ሠራተኞች የቤት አበል በአመልካች ድርጅት አለመወሰኑ የሠራተኞችን የእኩልነት መብት የሚጥስ ነው በማለት የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር በጽሕፈት ሥራ መደብ ላይ ላልሆኑ ሠራተኞች በወር ብር 800.00 አመልካች እንዲከፍል ወስኗል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም በጽሕፈት የሥራ መደብ ላይ ላልሆኑ ሠራተኞች የቤት አበል በድርጅቱ አልተወሰነላቸውም፣ የተለያየ የሥራ ደረጃ፣ ትምህርት ዝግጅትና ሥራ ልምድ ያላቸው ሰራተኞች የተለያየ የጥቅማጥቅም አበል መወሰኑ የእኩልነት መብትን የሚጥስ አይደለም፣ ውሳኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው የሚል ነው፡፡ የሰበር ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ ጉዳዩ በሥራ ክርክር ችሎት የሚታይ መሆን አለመሆኑ፣ የእኩልነት መብት አተገባበር ሊታዩ የሚገባቸው ሁኔታዎችን ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ ባቀረበው መልስ አስቀድሞ ክሱ ለአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ ቀርቦ ሥልጣን የለኝም ማለቱና በፌዴራል ከፍተኛ ውሳኔው የጸና እና አሁንም ጸንቶ የሚገኝ ስለሆነ ጉዳዩ በድጋሜ በጭበጥነት ተይዞ ሊታይ አይገባም፡፡ ጉዳዩ የወል ክርክር የሚሆነው ቀድሞ ያልነበረና አዲስ መብት ለመፍጠር የሚቀርብ ክርክር ሲሆን ነው፣ ተጠሪ ያቀረበው ክስ የበሰለ መብት እንዲከበር ወይም እንዲፈጸም በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ሥልጣን አለው፤ ውሳኔው ተገቢ ስለሆነ ሊጸና ይገባል ብሏል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሠበር አቤቱታውን አጠናክሮ ተከራክሯል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን የመመልከት ሥልጣን ያለው ማን ነው? የሚለውን በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ተጠሪ ሐምሌ 26 ቀን 2015 ዓ/ም ጽፎ ባቀረበው ክስ አመልካች ድርጅት ለሁሉም ሰራተኞች በሚል በተጻፈ ጥቅማጥቅም የተወሰነ መሆኑ ተገልጾ እያለ የቤት አበል በተለምዶ በጽሕፈት መደብ ላይ ያልሆኑ /non-clericals/ የሚሰሩ ሰራተኞች አልከፍልም ማለቱ የእኩልነት መብት የሚጥስ በመሆኑ የቤት አበል እንዲከፈል እንዲወሰን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክሱ ውድቅ የተደረገ ቢሆንም ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቤት አበል የተወሰነው የኑሮ ውድነትን ታሳቢ ያደረገ መሆኑ ከሰነዱ መረዳት ስለሚቻል በጽሕፈት መደብ ላይ ያልሆኑ ሠራተኞች የቤት አበል በአመልካች ድርጅት አለመወሰኑ የሠራተኞችን የእኩልነት መብት የሚጥስ ነው በማለት የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር በጽሕፈት ሥራ መደብ ላይ ላልሆኑ ሠራተኞች በወር ብር 800.00 አመልካች እንዲከፍል ወስኗል፡፡

አሁን አከራካሪ የሆነው ተጠሪ የጠየው ዳኝነትና ይግባኝ ሰሚ ችሎት የያዘው ጭብጥ የመመልከት ሥልጣን ያለው የሥራ ክርክር ችሎት ወይስ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ነው የሚለው ነው፡፡ የሥር የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የተመለከተው ተጠሪ ቀደም ሲል ክሱን ለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ አቅርቦ ሥልጣን የለኝም በማለት መወሰኑ፣ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔው መጽናቱና ይሕ ውሳኔ ያልተሻረ መሆኑን በመጥቀስ ነው፡፡ ጉዳዩ የግል ሥራ ክርክር ወይስ የወል ክርክር ነው፣ የትኛው አካል የሥረ-ነገር ሥልጣን አለው የሚለው ጉዳይ የሚመነጨው ከሕግ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ በአሠሪና ሠራተኛ ሕጉ መሠረት ሥልጣን ያለው መሆን አለመሆኑን መመርመር ሲገባው ቀድም ሲል ጉዳዩ የቀረበለት ወሳኝ ቦርድ ሥልጣን የለኝም ማለቱን ብቻ ተመልክቶ ማለፉ ተገቢ አይደለም፣ አሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርዱ ሥልጣን የለኝም ማለቱ ለሥራ ክርክር ችሎት የሥረ-ነገር ሥልጣን ምንጭ ሊሆን ስለማይችል ጉዳዩ በጭብጥነት ሊመረመር አይገባም በማለት ተጠሪ ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 139 ላይ በሥራ ክርክር ችሎት የሚታዩ ጉዳዮች የተዘረዘሩ ሲሆን በአንቀጽ 143 ደግሞ በአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ የሚመለከታቸው ጉዳዮች ተመልክተዋል፡፡ በድንጋጌዎቹ የተዘረዘሩት ዝርዝሮች እንደተጠበቁ ሆነው በሁለቱ የዳኝነት አካላት የሥልጣን ክፍፍል ዋነኛ መስፈርት ጉዳዩ የግል ወይም የወል ባሕሪ ያለው መሆን አለመሆኑ ላይ ነው፤ጉዳዩ የወል የሚሆነው ክስ ካቀረቡ ወገኖች ውጭ የሌሎች ሠራተኞችን መብትና ጥቅም የሚመለከትና በአዎንታዊ ሆነ በአሉታዊ ተፅዕኖ ያለው ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ ተፅዕኖው ክስ ባቀረቡ ሠራተኞች ላይ ብቻ የሚወሰን ከሆነ የግል የሥራ ክርክር ስለሚሆን በሥራ ክርክር ችሎት የሚታይ ይሆናል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 15531 እና በሌሎች መዛግብት የወልና የግል ሥራ ክርክር መስፈርት ላይ አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

ተጠሪ ሐምሌ 26 ቀን 2015 ዓ/ም ጽፎ ባቀረበው ክስ አመልካች ድርጅት ለሁሉም ሰራተኞች በሚል በተጻፈ ጥቅማጥቅም የተወሰነ መሆኑ ተገልጾ እያለ የቤት አበል በተለምዶ በጽሕፈት መደብ ላይ ያልሆኑ /non-clericals/ የሚሰሩ ሰራተኞች አልከፍልም ማለቱ የእኩልነት መብት የሚጥስ በመሆኑ የቤት አበል እንዲከፈል እንዲወሰን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የተጠሪ ዳኝነት አጠቃላይ በጽሕፈት መደብ ላይ ያልሆኑ ሠራተኞችን በሙሉ የሚመለከት ነው፡፡ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 246 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሠረት በይግባኝ ሰሚ ችሎት የተያዘው ዋናው ጭብጥ የአመልካች ድርጅት የወሰነውን መብት ሊፈጸም ይገባል ወይስ አይገባም የሚል ሳይሆን አመልካች ለሌሎች ሠራተኞች የቤት አበል ሲወሰን በጽሕፈት የሥራ መደብ ላይ ላልሆኑ ሠራተኞች የቤት አበል አለመወሰኑ የእኩልነት መብት የሚጥስ መሆን አለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡ ይሕ ጭብጥ በጽሕፈት የሥራ መደብ ላይ ላልሆኑ ሠራተኞች በአመልካች ያልተወሰነላቸውን የቤት አበል ሊያገኙ የሚገባ መሆን አለመሆኑን የሚወሰን አዲስ መብት የሚፈጥር እንጂ የተፈጠረ መብት ለማስከበር ባለመሆኑ ጉዳዩ የወል ክርክር ባሕሪ ያለው ነው፡፡ ስለሆነም ጉዳዩ የግል የሥራ ክርክርን የመመልከት ሥልጣን ባለው የሥራ ክርክር ችሎት የሚታይ ባለመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን የማየት ሥልጣን ሳይኖራቸው በሥረ-ነገሩ አከራክረው ውሳኔ መስጠታቸው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 316255 ሚያዚያ 21 ቀን 2016 ዓ/ም እና የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 155622 ታህሳስ 25 ቀን 2016 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1)(ለ) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. ተጠሪ ክሱን ለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ያቅርብ ብለናል፡፡

3. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- አፈጻጸሙ ላይ የተሰጠው እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ
- ውሳኔው መጋቢት 10 ቀን 2017 ዓ/ም በችሎት ተነቧል፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

የሰ/መ/ቁ 251519

የካቲት 24 ቀን 2017ዓ.ም

**ዳኞች ፡- ገበየሁ ፈለቀ**

**ዓለማየሁ ሹናራ**

**ደረጀ አያና**

**ኑረዲን ከድር**

**ብርሃኑ መንግሥቱ**

አመልካች፡- እስጢፋኖስ /ዩቡና/ ዲራጎ

ተጠሪ፡- የሲዳማ ክልል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ - ዐቃቤ ሕግ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ጉዳዩ አመልካች ከባድ የሰው ግድያ ወንጀል መፈጸሙ በማስረጃ ሳይረጋገጥ ጥፋተኛ ተብሎ በመቀጣቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል በቀረበ የሰበር አቤቱታ መነሻ የተደረገዉን ክርክር የሚመለከት ነዉ፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት በሲዳማ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች 2ኛ ተከሳሽ የነበረ ሲሆን ተጠሪ በአመልካች እና በሌሎች ተከሳሾች ላይ ያቀረበው ክስ ይዘት በአጭሩ፡- የአሁን አመልካች ከሌሎች ተከሳሾች ጋር በመሆን የወንጀል ሕግ አንቀጽ 539(1/ሀ) ሥር የተደነገገዉን በመተላለፍ በቀን 05/13/2013 ዓ.ም ከምሽቱ 4፡00 ሰዓት በሚሆንበት ጊዜ በሀዋሳ ከተማ መናኻሪያ ክፍለ ከተማ በፒያሳ ቀበሌ ልዩ ቦታው የእህል ወፍጮ አካባቢ ላይክ የሚባል ግሮሰሪ በረንዳ ላይ

ቁጭ ብለው ሳለ ሟች ፍሬው መልካሙን ሲጋራ አታጭስ ሲሉት ሟችም እስከዛሬ እያጨስኩ አይደለም ወይ ሲላቸው ለምን መልስ መለስክ በሚል ምክንያት ሟችን ተከትለው በመሄድ የስር 1ኛ ተከሳሽ ሟችን አንቆ ይዞ በእጁ በያዘው ቢላዋ የግራ ጆሮውን ከላይ በኩል በመውጋት 4x2 ሳ.ሜ የሚሆን ወደ ውስጥ 4 ሳ.ሜ እና በተጨማሪም ስፋቱ 6x3 ሳ.ሜ የሚሆን 3x2 ሳ.ሜ የሚሆን ወደ ውስጥ በመውጋት፤ እንዲሁም የግራ እጁን 2ኛ ጣት 4 ሳ.ሜ ስፋቱ 3x2 ሳ.ሜ በመውጋት ጉዳት አድርሰዋል፡፡ የአሁን አመልካች ደግሞ ሟችን ጀርባውን በግራ በኩል አጥንቱን በቢላዋ በመውጋት ስፋቱ 6x2 ሳ.ሜ ወደ ውስጥ 7 ሳ.ሜ የሚሆን ጉዳት በማድረስ ህይወቱ እንዲያልፍ አድርገዋል የሚል ነው፡፡ አመልካች ወንጀሉን አልፈጸምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ክዶ በመከራከሩ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች ተሰምተዋል፡፡

ፍ/ቤቱም በተከሳሾች የቀረበውን መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ የተጠሪን ምስክሮች እና የተከሳሾችን መከላከያ ምስክሮች ሰምቶ በሰጠው ፍርድ የአሁን አመልካች እና የስር 1ኛ ተከሳሽ ሟችን መግደላቸው በዓ/ህግ ምስክሮች መረጋገጡንና ክሱን ያልተከላከሉ መሆኑን ጠቅሶ የስር 1ኛ ተከሳሽን በሙሉ ድምጽ ጥፋተኛ ሲል የአሁን አመልካችን ደግሞ በአብላጫ ድምጽ ጥፋተኛ ነው ብሏል፡፡ ከዚህም በኋላ የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ከተቀበለ በኋላ እያንዳንዳቸውን በ19 አመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች በውሳኔው ቅር ተሰኝቶ ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ይግባኙ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ካደረገ በኋላ በሰጠው ውሳኔ የተጠሪ ምስክሮች የአሁን አመልካችን በተመለከተ የሰጡት ምስክርነት ቃል ሲታይ ምስክሮቹ የአሁን አመልካችን ፊቱን ለይተው እንዳላዩት እና ቁመቱንና ባህሪው እርሱን ይመስላል ማለታቸውን እንጂ ለይተው ያላወቁት መሆኑን፤ አመልካች የሰራውን ወንጀል በዝርዝር አለመመስከራቸውን፤ ይመስላል ማለት አመልካች ነው ለማለት የማይቻል መሆኑን፤ አመልካች በቦታው በመኖሩ ብቻ ወንጀሉን ሰርቷል ለማለት የማይቻል መሆኑን፤ የአመልካች መከላከያ ምስክር የሆነችው የግሮሰሪ ባለቤት ከውጭ ሰው ተወግቷል ግሮሰሪ ሊዘጋ ነው ከጓሮ በኩል ውጡ ስትላቸው መውጣቱን መመስከሯን፤ በዚህም ምክንያት ተጠሪ ባቀረበው ምስክር የአሁን አመልካች ድርጊቱን ስለመፈጸሙ ከጥርጣሬ በላይ አለማስረዳቱን ጠቅሶ የስር ከፍተኛ ፍ/ቤቱ የሰጠውን የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በመሻር አመልካች በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 149/2 መሰረት በነጻ እንዲሰናበት ወስኗል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታዉን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን የሰበር ሰሚ ችሎቱም ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት የአሁን አመልካች መልስ እንዲሰጥበት ካደረገ በኋላ በሰጠው ውሳኔ የተጠሪ ምስክሮች የአሁን አመልካች ከስር 1ኛ ተከሳሽ ጋር በመሆን ከሟች ጋር ሲታገሉ እንደነበር፤ ምስክሮቹ አመልካችን በችሎት ቆሞ ሳለ ለይተው ያላወቁት በወቅቱ ኮፍያ ያደረገ በመሆኑ ስለመሆኑ፤ አመልካች ድርጊቱ በተፈጸመበት ወቅት በቦታው ስለመኖሩ መመስከራቸውን፤ አመልካች በተጠሪ የቀረበውን ማስረጃ ማስተባበል ያልቻለ መሆኑን ጠቅሶ አመልካች ድርጊቱን ስለመፈጸሙ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

በተጠሪ ምስክሮች ተረጋግጦበታል በማለት የስር ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች በነጻ እንዲሰናበት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ አጽንቷል፡፡

አመልካች በቀን 26/11/2015ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት መጽናቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት ሲሆን ይዘቱ በአጭሩ - አመልካች ድርጊቱ በተፈጸመበት ቦታ ነበርኩኝ እንጂ ድርጊቱን አልፈጸምኩም፤ የተጠሪ ምስክሮች ድርጊቱን ስለመፈጸሜ አላስረዱብኝም፤ ባቀረብኩት ምስክር ወንጀሉን ያልፈጸምኩ መሆኑን አስረድቻለሁ፤የተጠሪ ምስክሮች እርሱን ይመስላል ከማለት ውጪ ድርጊቱን ስለመፈጸሜ አላስረዱም፡፡የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በማጽናት የወሰነዉ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 23/2 ስር በተደነገገዉ መሠረት የግድያ ወንጀል መፈጸሜ ሳይረጋገጥ በመሆኑ ዉሳኔዉ ከዚህ ድንጋጌ አፈጻጸም ጋር በተያያዘ በሰ/መ/ቁጥር 22069 ስር የተሰጠዉን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሚቃረን ነዉ፡፡ስለሆነም ተጠሪ ያቀረባቸው ምስክሮች አመልካች ድርጊቱን ስለመፈጸሜ ከጥርጣሬ በላይ ያላስረዱ ስለሆነ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ተሽሮ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ እንዲጸናል፡፡የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉ የጥፋተኝነት ውሳኔው የሚያጸና ከሆነም አንቀጹ ወደ ወንጀል ሕግ አንቀጽ 540 እንዲቀየርልኝ እና የ3ኛ አመት የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ስለሆንኩ ቅጣቱ በወ/ህ/አንቀጽ 192 መሰረት እንዲገደብልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ችሎቱ የአመልካችን የሰበር አቤቱታ እና የመጨረሻዉን ዉሳኔ መርምሮ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ ሰሚነት ስልጣኑ ማስረጃ መዝኖ አመልካች በክሱ የተጠቀሰውን ወንጀል ስለመፈጸሙ በበቂ ሁኔታ ባላስረዳበትና አመልካች ተከላከል ከተባለ በኋላም ወንጀሉን አለመፈጸሙን በማስረዳት ተከላክሎ እያለ ጥፋተኛ መባሉ ተገቢ አይደለም በማለት በነጻ እንዲሰናበት የወሰነውን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች ወንጀሉን ስለመፈጸሙ በማስረጃ ተረጋግጧል በሚል የሻረበትን አግባብነት ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ለ) እና በሲዳማ ክልል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 4/2012 አንቀጽ 12 ስር ለክልሉ ሰበር ችሎቱ ከተሰጠው ሥልጣን አንጻር እንዲመረመር ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ አዝዟል፡፡

ተጠሪ በቀን 04/04/2010 ዓ/ም በተጻፈ መልሱ - አመልካች ወንጀሉን ከስር 1ኛ ተከሳሽ ጋር መፈጸሙን ተጠሪ ባቀረባቸው ምስክሮች አስረድቷል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ ያስተላለፈዉን ዉሳኔ የሻረዉ የማስረጃ ምዘና መርህን ባልተከለተለ መልኩ ነው፡፡ወንጀሉ የተፈጸመዉ በምሽት በጨለማ ሲሆን አመልካች በወቅቱ ፊቱን ተሸፋፍኖ ኮፍያ አድርጎ ስለነበር መለየት አልቻልንም በማለት የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች መስክረዉ አሁን በችሎት ስናይ ከስር 1ኛ ተከሳሽ ጋር የቆመዉን ይመስላል በማለት ስለመሰከሩና ምስክሮች ከቦታዉ ሲደርሱ ሸሽተዉ መጥፋታቸዉን

አስረድተዋል፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ይህን ስህተት በማረም ማስተካከሉ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም፡፡ ስለሆነም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የክልሉን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዉሳኔ ማጽናቱ ተገቢ በመሆኑ እንዲጸናልን በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም የመልስ መልሱን በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

ከላይ አጠር ባለ መልኩ የተገለጸዉ በየደረጃዉ ባሉ የክልል ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ውሳኔዎች እንዲሁም የግራ ቀኙን ክርክር የሚመለከት ሲሆን እኛም አስቀድሞ የተያዘዉን ጭብጥ መሠረት በማድረግ አመልካች ክሱን እንዲከላከልና ጥፋተኛ ተብሎ እንዲቀጣ በመወሰኑ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የሕግ ስህተት መፈጸም አለመፈጸሙን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

በአገራችን በተዘረጋዉ የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሥርዓት መሠረት ሕገ-ወጥነቱና አስቀጪነቱ በሕግ የተደነገገዉን በማድረግ የሚፈጸም የወንጀል ድርጊትም ሆነ አል ድርጊት ሕጋዊ ተከሳሽ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮችን በአንድነት በሚያሟላ አኳኋን ስለመፈጸሙ በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ማስረዳቱ በፍርድ ቤት የተረጋገጠ እንደሆነ ተከሳሹ በወንጀል ሕጉ ወይም አግባብነት ባለዉ ሌላ ሕግ የተደነገገዉን ቅጣት መቀጣት ይገባዋል፡፡ በዚህ አግባብ ማንኛዉም ሰው በወንጀል ደርጊት ተጠያቂ የሚሆነው የተከሰሰበትን ድርጊት ወንጀል አድርጎ በሚደነግገዉ ሕግ ላይ በተመለከተዉ መሠረት ድርጊቱን ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት መፈጸሙ ለወንጀል ክርክር ተቀባይነት ባለዉ የማስረዳት ደረጃ ልክ በማስረጃ ሲረጋገጥ ነዉ፡፡ ስለሆነም በሌላ ልዩ ሕግ በተለየ ሆኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ተከሳሹ ጥፋተኛ ሆኖ እንዲቀጣ ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል ስለመፈጸሙ ዐቃቤ ሕግ ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች መሟላታቸዉን በሚያረጋግጥ አኳኋን አግባብነትና በሕግ ተቀባይነት ያለዉን ማስረጃ በማቅረብ ማስረዳት ይጠበቅበታል፡፡(በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 1፣2፣ 23፣ 58 እና 59 እንዲሁም የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 141 ፣ 142/1 እና 149 ስር የተደነገገዉ ይመለከቷል)፡፡

በሌላ በኩል የወንጀል ክስ የቀረበበት ሰዉ የወንጀል ድርጊት አለመፈጸሙ ወይም የወንጀል ሕጉ የወንጀል ተጠያቂነትን በሚያስከትለዉ ተካፋይነት ደረጃ በወንጀል አፈጻጸሙ ተካፋይ አለመሆኑ ሲረጋገጥ ከቀረበበት የወንጀል ክስ በነጻ የሚሰናበትበትን አግባብ በአገራችን የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡ ፍርድ ቤቶችም ክርክር ሲሰሙ፣ማስረጃ ሲመረምሩና ሲመዝኑ እንዲሁም ዳኝነት በተጠየቀበት ጉዳይ ላይ ዉሳኔ ሲሰጡ ከማንኛዉም ተጽዕኖ ነጻ በመሆንና ከሕግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ ሳይመሩ የወንጀል ሕጉን ግብ፣ ዓላማዎችና መርሆዎች ባከበረ እንዲሁም የተጎጂዉን፣የሕዝብና የመንግሥት መብትና ጥቅም ለማስከበር በሕግ ሥልጣን የተሰጠዉን ከሳሽ እና የተከሰሰዉን ሰዉ መብቶች በአግባቡ ባገናዘበ አኳኋን የቀረበላቸዉን የወንጀል ክስ፣ክርክር እና ማስረጃ አግባብነት ካለዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር አገናዝበዉ በመመርመር በገለልተኛነት እና በሙሉ ነጻነት የዳኝነት ተግባራቸዉን የማከናወን ግዴታ እና ኃላፊነት እንዳለባቸዉ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 9(1፣2፣ እና 4)፣13፣20፣37፣79(2 እና 3) ፣ከወንጀል ሕጉ ታላቅ ክፍል እና ከወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕጉ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን እና በይግባኝ ሰሚነት የሚዳኙ ፍርድ ቤቶች በሕግ በተሰጣቸዉ ሥልጣን መሠረት የማስረጃ አቀራረብን፣ አግባብነትን፣ ተቀባይነትን እና ማስረጃ አቅርቦ አንድን ፍሬ ነገር የማስረዳት ሸክም የሚመለከቱ መርሆዎች (Principles of Production, relevancy, admissibility and burden of proof of evidence) አተገባበር በሚቃረን አኳኋን እንዲሁም የማስረጃ ምዘናን ወይም የማስረዳት ደረጃን (standards of proof or weight of evidence) የሚመለከቱ መሰረታዊ መርሆዎች በመጣስ የመጨረሻ ዉሳኔ መስጠታቸዉ በግልጽ ሲረጋገጥ፤ በተጨማሪም በአንድ ማስረጃ ይዘት ላይ በግልጽ የተመለከተዉን ወይም በምስክሮች ተመስክሮ የተረጋገጠዉን በአግባቡ ያላገናዘበ እና ዉሳኔ የሚሻዉ የፍሬ ነገር ጭብጥ መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ አስፈላጊ ለሆነ ማስረጃ ተገቢዉን ዋጋ ሳይሰጡ ዉሳኔ ሲሰጡ፤ እንዲሁም በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠዉን ነጥብ ከሕጉ ጋር ሳያገናዝቡ መወሰናቸዉ ሲረጋገጥ ሰበር ችሎት ማስረጃ ወደ መመዘን ዉስጥ ገብቷል ሊባል እንደማይቻል እና እንደመሰረታዊ የሕግ ስህተት ተቆጥሮ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚገባ መሰረታዊ የሕግ ስህተት እንደሆነ በሰ/መ/ቁጥር 113464 (ቅጽ 19)፣ 225975፣ 246157 እና 228017 (ያልታተሙ) መዛግብት ላይ ይህ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

ከላይ ከማስረጃ ሕግ መርሆዎች አተገባበር ጋር በተያያዘ የፌዴራልም ሆነ የክልል ሰበር ችሎቶች ያላቸዉ ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የፌዴራልም ሆነ የክልል ሰበር ችሎቶች በኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ እና ለ)፣በተያዘዉ ጉዳይ የሲዳማ ክክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሲዳማ ብሔራዊ ክልል ሕገ መንግስት አንቀጽ 65(2/ለ) እንዲሁም በሲዳማ ብሔራዊ ክልል መንግስት ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 4/2012 አንቀጽ 12(1 እና 2) ስር በተደነገገዉ መሰረት ሥልጣን የተሰጠዉ በክልላዊ ጉዳይ ላይ በተሰጠ የመጨረሻ ዉሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ሲኖር ስህተቱን የሚያርም ዉሳኔ መስጠት እንዲችል ብቻ ነዉ፡፡ አንድ አከራካሪ ፍሬ ነገር መኖር አለመኖሩን ማስረጃዎችን መርምረዉ እና መዝነዉ አረጋግጠዉ ዉሳኔ እንዲሰጡ በሕግ ሥልጣን የተሰጣቸዉ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣን እና በይግባኝ ለሚዳኙ ለክልሉ ፍርድ ቤቶች ወይም ለሌላ ዳኝነት ነክ ሥልጣን ለተሰጠዉ አካል ብቻ ነዉ፡፡በመሆኑም ተከራካሪ ወገኖች ማስረጃ ለመቀበል፣ ለመስማትና ለመመዘን ሥልጣን ለተሰጣቸዉ ፍርድ ቤቶች ያቀረቡትን ማስረጃዎች የመመዘን ጉዳይ ዉስጥ በመግባት ማስረጃዎችን በመመርመርና በመመዘን አከራካሪ የሆነዉ ፍሬ ነገር መኖር አለመኖሩን ወይም ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል የሚመለከት ግዙፋዊ ፍሬ ነገር ፈጽሟል ወይስ አልፈጸመም የሚለዉን ማስረጃዎችን መርምሮና መዝኖ በማረጋገጥ ዉሳኔ መስጠት መሰረታዊ የሕግ ስህተት እንደማረም የሚቆጠር ባለመሆኑ በክልል ሰበር ሥልጣን ማዕቀፍ ዉስጥ የሚታይ አይደለም፡፡

በያዝነዉ ጉዳይ አመልካች ላይ ክሱ የቀረበዉ አመልካች ከሌሎች ተከሳሾች ጋር በመሆን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1/ሀ) እና 539(1/ሀ) ስር የተደነገገዉን በመተላለፍ ሟችን ጀርባውን በግራ በኩል አጥንቱን

በቢላዋ በመውጋት ስፋቱ 6x2 ሳ.ሜ ወደ ውስጥ 7 ሳ.ሜ የሚሆን ጉዳት በማድረስ ህይወቱ እንዲያልፍ አድርገዋል በሚል ነዉ፡፡ በዚህ መሠረት አመልካች በወንጀሉ አፈጻጸም በዋና ወንጀል አድራጊነት ተሳትፎ አድርጓል በሚል እስከተከሰሰ ድረስ በቀጥታ ወይም በእጅ አዙር በሚች ግድያ ላይ በእርግጥም ተሳትፎ የነበረዉ ስለመሆኑ እና የነበረዉንም ተሳትፎ ደረጃ ወይም አይነት ቢያንስ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 141 ስር ተመላክቶ በተደነገገዉ ልክ በቂና አሳማኝ ማስረጃ በማቅረብ ዐቃቤ ሕግ ማስረዳት ይጠበቅበታል፡፡

ዐቃቤ ሕግ በዚህ ልክ ማስረዳት ካልቻለ አመልካች ክሱን እንዲከላከል ግዴታ መጣል በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23/2 ስር የተደነገገዉን መሠረታዊ መርህ መቃረን ከመሆን ባለፈ የማስረጃ ምዘና ፣ የማስረዳት ደረጃ እና ሸክም የሚመለከቱ መሠረታዊ መርሆዎችን መጣስ ስለሚሆን ሊታረም የሚገባዉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ይሆናል፡፡በተያያዘዉ ጉዳይ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሕግ የተሰጠዉን ማስረጃ የመመርመርና የመመዘን ሥልጣኑን በመጠቀም የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች የሰጡትን ምስክርነት ቃል መርምሮና መዝኖ ምስክሮቹ የአመልካችን ፊት ለይተው እንዳላዩት እና ቁመቱንና ባህሪው እርሱን ይመስላል ማለታቸውን እንጂ ለይተው ያላወቁት መሆኑን፤ አመልካች የሰራውን ወንጀል በዝርዝር አለመመስከራቸውን፤ ይመስላል በማለት የመሰከሩትም ቢሆን አመልካች ነው ለማለት የማያስችል በመሆኑና አመልካች በቦታው መኖሩ ብቻዉን አመልካች ወንጀሉን ፈጽሟል ለማለት አያስችልም የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡በዚህ መሠረት ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት ማስረጃ መርምሮና መዝኖ የደረሰበት ድምዳሜ የሕጉን ግዙፋዊ አላባ (ፍሬ ነገር) የሚመለከት ድምዳሜ በመሆኑ የማስረጃ ምዘና መርህ አተገባበር ስህተት የተፈመበት መሆኑ ካልተረጋገጠ በስተቀር በዚህ ችሎትም ሆነ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ተቀባይነት ሊኖረዉ ይገባል፡፡

ከላይ የተመለከተዉ የክልሉ ሰበር ችሎት ዉሳኔ ላይ የታየዉ ስህተት እንደተጠበቀ ሆኖ አመልካች ክሱን እንዲከላከል ከታዘዘ በኋላም ቢሆን የተጠሪ ምስክሮች ወንጀሉ ተፈጸመ በተባለበት ቦታና ጊዜ አመልካች በቦታው መኖሩን ያስረዱ ቢሆንም በይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት የምስክሮቹ ቃል ተመዝኖ እንደተረጋገጠዉ አመልካች በቦታዉ በመገኘቱ ብቻ ወንጀሉን ሰርቷል ለማለት የማይቻል መሆኑን፤ የአመልካች መከላከያ ምስክር የሆነችው የግሮሰሪ ባለቤት ከውጭ ሰው ተወግቷል ግሮሰሪ ሊዘጋ ነው ከንሮ በኩል ውጡ ስትላቸው መውጣቱን ከመሰከረችዉ ጋር ተገናዝቦ ሲታይ አመልካች በቦታዉ የተገኘዉ መጠጥ ሲጠጡ ስለነበር በማረጋገጡ አመልካች የተከሰሰበትን የወንጀል ድርጊት አለመፈጸሙ በፍሬ ነገር ደረጃ አረጋግጧል፡፡ አመልካች ወንጀሉ በተፈጸመበት ቦታ የተገኘዉ በተጠቀሰዉ ምክንያት መሆኑ በተረጋገጠበት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች ወንጀሉ በተፈጸመበት ቦታ እንደነበር መመስከሩን እና ምስክሮቹ አመልካችን በችሎት ቆሞ ሳለ ወንጀሉ በተፈጸመበት ጊዜ ኮፍያ አድርጎ የነበረዉን ሰዉ ተከናንቦ የነበረ ከመሆኑ የተነሳ አመልካች ይሁን ሌላ ሰዉ ለይተዉ አመልካች ነዉ በማለት ባልመሰከሩበት አመልካች የተመሰከረበትን አልተከላከለም ሲል የደረሰበት ድምዳሜ በምስክሮች ተመስክሮ የተረጋገጠዉን ፍሬ ነገር ያላገናዘበና ማስረጃ የመመዘን ተግባር ዉስጥ መግባቱን የሚያሳይ ነዉ፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

ሲጠቃለል አመልካችን ጥፋተኛ በሚያደርግ ልክ አመልካች በሟች ግድያ ላይ የነበረዉን ተሳትፎ የተጠሪ ምስክሮች ባላስረዱበት የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ክሱን አልተከላከለም በሚል የጥፋተኝነት ፍርድ እና የቅጣት ዉሳኔ ማስተላለፉ ሊታረም የሚገባዉ ስህተት ነዉ፡፡እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሕግ ማስረጃ እንዲመረመርንና እንዲመዘን የተሰጠዉን ስልጣን በመጠቀም ማስረጃዎችን በመመዘን አመልካች በግድያ ወንጀሉ ተካፋይ መሆኑን በሚያሳይ መልኩ ተጠሪ በምስክሮቹ አላስረዳም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ ሕግን የተከተለ ሆኖ እያለ የክልሉ ሰበር ችሎት የተጠሪ ምስክሮች አመልካችን በግድያ ወንጀሉ ተሳትፎ እንደነበረዉ ማስረዳታቸዉን ከምስክሮቹ ቃል እንደተረዳ በመግለጽ የይግባኝ ሰሚዉን ችሎት ዉሳኔ በመሻር የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ዉሳኔ ማጽናቱ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 23/2 ስር የተደነገገዉን የወንጀል ሕግ መሠረታዊ መርህ፣ከማስረጃ ምዘና መርህ አተገባበር ጋር በተያያዘ ከላይ በተጠቀሱት መዛግብት ላይ በዚህ ሰበር ችሎት የሰጠዉን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ፣ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 141 ስር የተደነገገዉን የማስረጃ ምዘና ደረጃ ያልተከተለ ብቻ ሳይሆን በፌዴራል እና በክልሉ ሕግጋተ መንግሥታት ፣ እንዲሁም በክልሉ ፍርድ ቤቶች አዋጅ ላይ ለክልሉ ሰበር ችሎት ከተሰጠዉ ስልጣን ዉጭ በሆነ አግባብ ማስረጃን በመመዘን የተሰጠ ዉሳኔ በመሆኑ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሀ እና ሸ) እና 10(1/ሐ) መሠረት ሊታረም የሚገባዉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 31498 ላይ በቀን 14/06/2014ዓ.ም እና በቀን 11/08/2014ዓ/ም በአመልካች ላይ ያስተላለፈዉን የጥፋተኝነት ፍርድ እና የቅጣት ዉሳኔ የሲዳማ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 04503 ላይ በቀን 26/08/2015ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ ማጽናቱ ስህተት በመሆኑ በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የሲዳማ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 03420 ላይ በቀን 11/02/2015ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 መሰረት ጸንቷል፡፡
3. በአመልካች ላይ የተላለፈዉ የጥፋተኝነት ፍርድም ሆነ የቅጣት ዉሳኔ ተሽሮ አመልካች በነጻ እንዲሰናበት ተወስኗል፡፡

## ትዕዛዝ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ እንዲያዉቀዉ ለሲዳማ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ይተላለፍ፡፡ ለግራ ቀኙም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. በዚህ የፍርድ ዉሳኔ መሠረት እንዲፈጽም የዉሳኔዉ ግልባጭ አመልካች ታስሮ ለሚገኝበት ማረሚያ ቤት ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ዳኞች፡-ገበየሁ ፈለቀ

አለማየሁ ሹናራ

ደረጀ አያና

ኑረዲን ከድር

ብርሃኑ መንግስቱ

አመልካቾች፡- የፌደራል ዐቃቤ ህግ ጠበቃው መላኩ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አበበ ወንድሙ ኤጋ ከጠበቃ አንዳምላክ ሹምዬ ጋር ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች በ01/12/2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.279603 በ25/11/2014 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.234190 በ02/09/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ፍርድ በማፅናት መወሰኑ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለታቸው ሲሆን በስር ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ከሳሽ ሆነው ተጠሪ ተከሳሽ ሆነው በሰው መግደል የወንጀል ጉዳይ በስር ፍርድ ቤት ተከራክረዋል፡፡

አመልካች በስር ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ ባቀረበው ክስ ተጠሪ የወ/ህ/ቁ.539(1)(ሀ) ን ተላልፈው ሰው ለመግደል አስቀድሞ በነበረው ሀሳብ ጨካኝነቱንና ነውረኝነቱን በሚያሳይ ሁኔታ ወንድሙን ሟች ጀንበሩ ወንድሙን ከአሁን በፊት ሰድቦኛል እንዲሁም በሚያሽከረክረው መኪና ሊገጨኝ ሞክሯል በማለት በቂም በቀል በመነሳት ሽጉጥ ተኩሶ ማጅራቱን ሲመታው ሲወድቅ በተደጋጋሚ ሶስት ጊዜ ተኩሶ ግንባሩን በቀኝ በኩል አንገቱንና በግራ በኩል አንገቱን በመምታት የጥይት እርሳስ ጉዳት በራስ ቅሉ የኋለኛው ክፍል፣የክብ ቅርፅ ያለው ጥይት እርሳስ የገባበት ቁስል በራስ ቅሉ የኋለኛው ክፍል፣ሳተላይት ቅርጽ ያለው የጥይት እርሳስ የወጣበት ቁስል፣በግራ ግንባሩ የፊተኛው ክፍል ላይ የአጥንት መሰበር ጉዳት፣በራስ ቅሉ ፊተኛው የታችኛው ክፍል ላይ እንዲደርስበት፣የመበሳት ጉዳት በአንገቱ ላይ እንዲደርስበት ፣በአንጎሉ የላይኛው ሽፋን ክፍል የተሰራጨ የደም መፍሰስ እንዲሁም የአየር ባንቧው የመበለዝ ጉዳት እና በዙሪያው ከፍተኛ ደረጃ ያለው የውስጥ ደም መፍሰስ ጉዳት እንዲደርሰበት እና ህይወቱ እንዲያልፍ አድርጎ በዚህም ከባድ የሆነ የሰው ግድያ ወንጀል ፈፅሟል በማለት ከሷል፡፡

ዐቃቤ ህግ በ2ኛው ክሱም ተጠሪ የጦር መሳሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀጽ 22(2) ተላልፎ የፀና ፈቃድ ሳይኖረው ሽጉጥ በመያዝ ሟች ጀንበሩ ወንድሙን ተኩሶ በመምታት ህይወቱ እንዲያልፍ አድርጓል፤በዚህም ፈቃድ ሳይኖር የጦር መሳሪያ መያዝና መገልገል ወንጀል ፈፅሟል በማለት ከሷል፡፡

ተጠሪ ክሱ ተነቦለት እንዲረዳው ከተደረገ በኋላ መቃወሚያ የለኝም ድርጊቱን ፈፅሜያለሁ፤ሟች በ2012 ዓም በመኪና ገጭቶኝ ከስሼው ነበረ፤ሰኔ 10 ቀን 2013 ዓም ከስራ ወደ ቤቴ ስሄድ በመኪና ሊገጨኝ ከኋላ እየፈጠነ ሲመጣ አመለጥኩት፤በ2012 ዓም ሽጉጥ ይዞ ቤቴ ድረስ በመምጣት ሊመታኝ ነበረ፤ከሟች ጋር በይዞታ ምክንያት አለመግባባት ነበረን፤፤ሰኔ 10 ቀን 2013 ዓም ለ3ኛ ጊዜ በመኪና ሊገጨኝ ብሎ ሲስተኝ በንዴት ውስጥ ሆኜ የአያቴን ሽጉጥ ይዤ በመሄድ ሟችን ጠብቄ በመኖሪያ አካባቢያችን ሽገር ማዞሪያ አካባቢ ከቀኑ 11፡30 ላይ አግኝቼው አራት ጊዜ ጭንቅላቱ ላይ በመተኮስ መትቼዋለሁ በማለት አስመዝግቧል፡፡ዐቃቤ ህግ እንደ ክሱ ስላላመነ ምስክሮቼን ላሰማ በማለት ስለጠየቀ የአቃቤ ህግን 4 ምስክሮች ሰምቶ የሰነድ ማስረጃዎችን መርምሮ በቀረበባቸው ክስ ስር እንዲከላከሉ ብይን ሰጥቶ ተጠሪም ሶስት የመከላከያ ምስክሮችን አቅርቦ አስምቷል፡፡

ፍርድ ቤቱ ይህንን ተከትሎ በሰጠው ውሳኔም በሟችና በተጠሪ መሀከል በይዞታ ፀብ የነበረ መሆኑን፤በዚህም ምክንያት ሟች ተጠሪን ለመግደል ተደጋጋሚ ሙከራ ያደረገበት መሆኑን ምስክሮቹ ያስረዱ መሆኑን፤የወንጀል ድርጊቱ የተፈፀመው ሰኔ 10 ቀን 2013 ዓም ከቀኑ 11፡30 እስከ 12፡00 ሆኖ ሟች ተጠሪን በዚሁ እለት ከቀኑ በግምት ከ9፡30 እስከ 10፡30 ባለው ጊዜ ውስጥ በተደጋጋሚ ያደረሰበት በደል ሳያንሰው በመኪና ሊገጨው የነበረ መሆኑ ተጠሪ የወንጀል ድርጊቱን በከፍተኛ ስሜት እና በንዴት ላይ ሆኖ የፈፀመው መሆኑን የሚያሳይ መሆኑን ይህም ለጉዳዩ አግባብነት ያለው በከባድ የሰው ግድያ የሚቀጣው ድንጋጌ ሳይሆን የወ/ህ/ቁ.541 ነው በማለት በዚሁ ድንጋጌ ስር ተጠሪን ጥፋተኛ በማለት፤2ኛውን ክስ አስመልክቶ በተመሳሳይ ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ በማለት በሶስት አመት ከሶስት ወር ቀላል እስራትና በአንድ ሺህ ብር የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ በአብላጫ ድምፅ ወስኗል፡፡ይህ ውሳኔ ጉዳዩን በይግባኝ በተመለከተው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ፀንቷል፡፡

አመልካችም የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት በ01/12/2015 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ለዚህ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ይዘቱም፡-የመከላከያ ምስክሮቹ በመኪና ሊገጨው የሞከረው ወንድሜ ነው ብሎ ተጠሪ የነገራቸው መሆኑን ከማስረዳት ባለፈ መኪናውን ይነዳ የነበረው ሟች ስለመሆኑ በራሳቸው አረጋግጠው የሰጡት የምስክርነት ቃል የለም፡፡ተጠሪ የነገራቸውም ለራሱ በሚጠቅም መልኩ ሲሆን የተከሳሽነት ቃሉም ተጠሪን በሚጠቅም መልኩ የቀረበ፤በምርመራ ወቅት በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ.27(2) እና 35 መሰረት ተጠሪ የሰጠውን ቃል የማያስተባብል ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤቶች ለወ/ህ/ቁ.541(ለ) የተሳሳተ ትርጉም በመስጠት ተጠሪ ንዴቱ የሚበርድበት ጊዜ እያለው በወ/ህ/ቁ.541 ስር

ጥፋተኛ መባሉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ውሳኔው ተለውጦ በወ/ህ/ቁ.539(1)(ሀ) ስር የጥፋተኝነት ውሳኔ ይሰጥልኝ የሚል ነው፡፡

አቤቱታው የቀረበለት የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ለዚህ ችሎት ከመራው በኋላ ይህ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ፦በስር ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ የወ/ህ/ቁ.539(1)(ሀ) ተጠቅሶ የቀረበው ክስና በማስረጃ ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር አንፃር የስር ፍርድ ቤቶች ክስ የቀረበበትን ድንጋጌ ለመለወጥ የጠቀሱት ምክንያት እና የወ/ህ/ቁ.541(1)(ለ) ድንጋጌን የተረጎሙበትን አግባብ ለመመርመር ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ይቅረብ፡፡ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክራቸውን ይለዋወጡ በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ በዚህ አግባብ በ16/03/2015 ዓም የተፃፈ መልስ ያቀረበ ሲሆን በዚህ መልሱም የወንጀል ድርጊቱ የተፈፀመበት ጊዜና ሟች የግድያ ሙከራ ያደረገበት ሰዓት ተከታታይነት ያላቸው በተከታታይነት በተመሳሳይ እለት እና ያለመቆራረጥ የተፈፀሙ ድርጊቶች በመሆናቸው የወንጀል ድርጊቱንም የፈፀምኩት በደም ፍላትና በንዴት ውስጥ ሆኜ በመሆኑ፤ከተከታታይነቱ አንፃር በቂም በቀል ተፈፀመ ሊባል የማይችል በመሆኑ፤እነዚህ የተጠሪ የደም ፍላት፤ንዴትና ከፍተኛ ስሜት መመዘኛዎች በማስረጃ የተረጋገጡ በመሆናቸው፤ተጠሪ ድርጊቱን የፈጸምኩት ሟችን ለመጉዳት አስቤ ሳይሆን በተሰማኝ አስከፊ የሆነ የስሜት ጭንቀትና ንዴት ምክንያት በመሆኑ፤ተጠሪ በድርጊቱ ተፀፅቼ፤የእስራት ጊዜዬን ጨርሼ ወደ ማህበረሰቡ የተቀላቀልኩኝ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት እነዚህን ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የሰጠው ውሳኔ ሊፀና እና የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካች ታህሳስ 01 ቀን 2017 ዓም የተፃፈ የመልስ መልሱን በማቅረብ ክርክሩን አጠናክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለፀውን ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ፣ ከጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እና ቅሬታው ለሰበር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ነጥብ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተው መርምሮታል፡፡ዐቃቤ ህግ በተጠሪ ላይ ክሱን ያቀረበው የወ/ህ/ቁ.539(1)(ሀ) ን መሰረት በማድረግ ሲሆን አንድ ሰው በዚህ ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ ሊባል የሚችለው ሰውን ለመግደል አስቀደሞ የነበረውን ሀሳብ ወይም ምክንያት፤ለመግደል የተጠቀመበትን መሳሪያ ወይም ዘዴ፣ የአገዳደሉን ሁኔታ አልያም ሌላ ቅጣቱን ሊያከብድ የሚችል ምክንያት ተገኝቶ ይህ ምክንያት ድርጊት ፈፀሚው ጨካኝ፤ነውረኛ ወይም አደገኛ መሆኑን የሚያሳይ ሆኖ ሲገኝ መሆኑን የድንጋጌው አጠቃላይ ይዘት ያሳያል፡፡የወንጀል ድርጊቱ አፈፃፀም ከላይ በተመለከተው አግባብ ቢሆንም፤ከባድ የሰው ግድያ የፈፀመው ሰው የወንጀል ድርጊቱን የፈፀመው ከፍ ባለ ደም በሚያፈላ ምክንያት ወይም ባልጠበቀው ህሊናን በሚያውክ ድንገተኛ ምክንያት ወይም በከፍተኛ ስሜት ወይም በብርቱ ዝንባሌ የተነሳ ሆኖ እነዚህ ሁኔታዎች መኖራቸው በአንድ ምክንያታዊ ሰው ምክንያታዊ

ግምገማ ከተረጋገጠ የጥፋተኝነት ውሳኔው ሊሰጥ የሚገባው በወ/ህ/ቁ.539(1)(ሀ) ስር ሳይሆን በወ/ህ/ቁ.541(ለ) መሰረት መሆኑን ከድንጋጌዎቹ የጋራ ንባብ የምንረዳው ነው፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ የግድያ ወንጀል ድርጊቱን በወንድማቸው ጀንበሩ ወንድሙ ላይ የፈፀሙት በእለቱ በሟች የተፈፀመባቸው ህሊናን በሚያውክ ድንገተኛ ና ከፍተኛ ስሜት ውስጥ በሚያስገባ የግድያ ሙከራ ምክንያት መሆኑን ይህ ደምን የሚያፈላ የሟች ተግባር ራሳቸውን እንዳይቆጣጠሩ ያደረጋቸው መሆኑን ገልፀው እየተከራከሩ በመሆኑ ለጉዳዩ ተገቢውን ድንጋጌ ለመምረጥ ይህ የወንጀል ሀላፊነትን የሚቀንስ ተግባር መፈፀሙ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ በመሰረቱ ደም ፍላትን የሚያስከትል ተግባር በሟቹ የሚፈፀሙ አንድ ወይም ተከታታይነት ያላቸውን ድርጊቶች የሚወክል ሆኖ በአንድ ምክንያታዊ ሰው እይታ ድንገተኛ እና ጊዜያዊ በሆነ ሁኔታ በራሱ ላይ ያለውን ራስን መቆጣጠርን ስልጣን የሚያሳጣ ተግባር መሆኑን የዘርፉ የተለያዩ ፀሀፍት የሚገልፁ ሲሆን ደም ፍላትን የሚያስከትል ተግባር በሟቹ ተፈፅሟል ወይስ አልተፈፀመም የሚለውን በአግባቡ ለመመለስ ግን ሶስት መሰረታዊ ሁኔታዎች ሊሟሉ የሚገባ መሆኑን ፀሀፍት በተለያዩ ፅሁፎቻቸው ያመለክታሉ፡፡ ስለሆነም ደም ፍላትን የሚያስከትል ተግባር በሟቹ ተፈጽሟል በማለት የግድያ ወንጀል ፈፅሟል በተባለው ሰው ላይ የቀለለ ሀላፊነት ሊጣል የሚችለው በሟች የተፈፀመው ተግባር አንድ ምክንያታዊ ሰውን ራሱን እንዳይቆጣጠር የሚያደርግ መሆኑ፤በዚህ ተግባር ምክንያት በወቅቱ የወንጀል ድርጊት ፈፃሚው በርግጥም ራሱን የማይቆጣጠርበት ሁኔታ ውስጥ የነበረ መሆኑ (in fact the accused lose control as a result of these provocative acts) እንዲሁም ድርጊቱ በፍጥነትና ምንም የመረጋጊያ ጊዜ ሳይሰጥ የተፈፀመ መሆኑ (The response was sudden and there was no time for passions to cool) ሲረጋገጥ ሊሆን ይገባል፡፡

አሁን የያዝነውን ጉዳይ ከነዚህ መስፈርቶች አንፃር ስናየው የተጠሪ 1ኛ ምስክር ሟች ተጠሪን በ2012 ዓም በመኪና ሊገጨው በሽጉጥም ሊገድለው የነበረ መሆኑን በመጨረሻም በመኪና ሊገጨው ሲል አምልጦ ሟችን የገደለው መሆኑን (Cumulative Provocation) መኖሩን በሚያሳይ መልኩ ያስረዱ መሆኑ ማስረጃን የመስማት፤የመመርመርና የመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ቢሆንም፤2ኛ እና 3ኛ የመከላከያ ምስክሮች የወንጀል ድርጊቱ በተፈፀመበት እለት ከቀኑ 9:30 ተጠሪ ወንድሜ ነው ብሎ የገለፀላቸው ሰው ተጠሪን በመኪና ሊገጨው ሲል ዘሎ ያመለጠው መሆኑን ያስረዱ ቢሆንም የመግጨት የመኩራ ድርጊቱ የወንጀል ድርጊቱ ሲፈፀም በቀጥታ የተመለከተው 1ኛ የዐቃቤ ህግ ምስክር ተጠሪ ሟችን መግደሉን ከገለፀበት ሰዓት 11:30 ጋር የሁለት ሰዓት ልዩነት ያለው መሆኑ፤ እንዲሁም ተጠሪ የእምነት ክህደት ቃላቸውን ሲሰጡ ከመግደል ሙከራው ከተረፉ በኂላ ወደ ቤት በመሄድ የአያታቸውን ሽጉጥ በመያዝ፤በመኖሪያ አካባቢያቸው ሟችን ጠብቀው የገደሉ መሆኑን መግለፃቸው የወንጀል ድርጊቱን ራሳቸውን የማይቆጣጠሩበት ሁኔታ ውስጥ ቆይተው በሁለቱ ድርጊቶች መካከል ምንም የመረጋጊያ ጊዜ ሳይኖር የፈፀሙት ነው ከማስባል ይልቅ በመጨረሻ

በተፈፀመባቸው ድርጊትና በቀደሙት ድርጊቶች ቂም በመያዝ ሰፊ የመረጋጊያ ጊዜ እያላቸው የወንጀል ድርጊቱን የፈፀሙ መሆኑን እያሳየ፣ሲጠቃለልም ተጠሪ ደም ፍላትን ሊያስከትል የሚችል የመግደል ሙከራ በሟች ተፈፅሞባቸው በዚህ ድርጊትና በሟች ላይ በፈፀሙት ከባድ የሰው ግድያ ተግባር መሃል ያለው የጊዜ ልዩነት በጣም አጭር ሆኖ በፍጥነትና ምንም የመረጋጊያ ጊዜ ሳያገኙ ራሳቸውን የማይቆጣጠሩበት ሁኔታ ውስጥ ቆይተው ከባድ የሰው መግደል የፈፀሙ መሆኑን ባላስረዱበት፣የቀረቡት ማስረጃዎች ከዚህ በተቃራኒ እያሳዩ የስር ፍርድ ቤቶች ድንጋጌውን በመቀየር በወ/ህ/ቁ.541(ለ) ስር ጥፋተኛ ማለታቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ይኸው ታርሞ ተጠሪ ጥፋተኛ ሊባሉ የሚገባው በወ/ህ/ቁ.539(1)(ሀ) ስር ነው በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ቅጣትን በተመለከተ በሁለቱም የወንጀል ክሶች የተመለከቱት የእስራት ቅጣቶች ሲደመሩ በወ/ህ/ቁ.539(1)(ሀ) ከተመለከተው እርከን 39 ሊያልፍ ስለማይችል ይህንኑ በመውሰድ ከእርከን 39 ላይ ደግሞ በስር ፍርድ ቤቶች በተያዙት 6 ማቅለያ ምክንያቶች ምክንያት 6 እርከን ሲቀነስ እርከን 33 ላይ የሚያርፍ ሲሆን እርከን 33 ደግሞ ከ14 አመት እስከ 16 አመት ከ10 ወር የሚያስቀጣ በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ውሳኔ**

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.279603 በ25/11/2014 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔና ይህንን ውሳኔ በማፅናት የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.234190 በ02/09/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስነስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9(1)(ለ) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪ በወ/ህ/ቁ.539(1)(ሀ) ስር በከባድ የሰው ግድያ ወንጀል ጥፋተኛ ናቸው ብለናል፡፡
3. ተጠሪ በወ/ህ/ቁ.539(1)(ሀ) ስር በከባድ የሰው ግድያ ወንጀል እና በአዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀፅ 22(2) ስር ጥፋተኛ የተባሉ በመሆኑ በዚህ ጉዳይ የታሰሩት ታስቦ በ14 ዐመት ፅኑ እስራትና በብር 1,000.00 እንዲቀጡ ተወስኗል፡፡

**ትዕዛዝ**

1.የክፍሉ ፖሊስ ተጠሪን በመያዝ ለክፍሉ ማረሚያ ቤት እንዲያስረክብና የአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት የእስራት ቅጣቱን ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ታዟል፡፡

2.የዉሳኔዉ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ሲጠይቁ ለግራ ቀኙም ይሰጣቸዉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
## የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መዝገብ ቁጥር - 266395

ቀን - 26/06/2017 ዓ.ም

ዳኞች - ገበየሁ ፈለቀ

ዓለማየሁ ሹናራ

ደረጀ አያና

ኑረዲን ከድር

ብርሃኑ መንግስቱ

አመልካች - አቶ መሀመድ አለሙ አልቀረቡም

ተጠሪ - የኦሮሚያ ጠቅላይ አቃቤ ህግ አበራ ገለታ ቀረቡ

መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው ለምርመራ ስለሆነ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

### ፍርድ

ይህ ጉዳይ የቀረበው አመልካች በ 13/10/2016 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በተጠሪ ያልተነሳውን የቅሬታ ነጥብ በራሱ በማንሳት የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል የገደብ ውሳኔን ውድቅ በማድረግ የእስራት ቅጣቱን እንዲፈፀም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት ይህንን ውሳኔ ለማስለወጥ ነው፡፡

ጉዳዩ የቀረበው የኦሮሚያ ክልል ሸገር ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች 1ኛ ተከሳሽ አሁን የክርክሩ አካል ያልሆነው የትኦትኦ የልብስ ስፌት ፋብሪካ ኃ/የተ/የግ/ማ 2ኛ ተከሳሽ ተጠሪ ከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ በስር ፍርድ ቤት ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበው 1ኛ ክስ የወ/ህግ አንቀፅ 32(1)(ሀ)፣

**ማስታወሻ፡** - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

34(1) እና 693(1) በመተላለፍ በትኦትኦ የልብስ ስፌት ፋብሪካ ኃ/የተ/የግ/ማ ውስጥ የፋብሪካው ኃላፊ እና ባለንብረት ሆኖ በሚሰሩበት ጊዜ ለግል ተበዳይ አቶ ሽምሱ አወል የብር አምስት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሺህ ከኦሮሚያ ህብረት ስራ ባንክ የሚመነዝር ቼክ ሰጥቶ የግል ተበዳይ ገንዘቡን ለማውጣት ወደ ባንክ ሲሄድ በቂ ገንዘብ የለውም በመባሉ ገንዘቡን ሊያገኝ አልቻለም፡፡ ስለዚህ በቂ ስንቅ ሳይኖር ቼክ በመስጠት ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡ አመልካች የወንጀሉን ድርጊት አልፈፀምኩም ብሎ ክዶ በመከራከሩ ተጠሪ የሰውና የሰነድ ማስረጃ አቅርቦ እንደ ክስ አቀራረቡ አስረድቷል፡፡ አመልካች እንዲከላከል ታዞ መከላከያ ማስረጃ ያቀረበ ሲሆን የአመልካች መከላከያ ምስክሮች ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቼክ መጥፋቱን አስረድተዋል፡፡

የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ ተሰምቶ ከተጠናቀቀ በኃላ መዝገቡን መርምሮ አመልካች በተከሰሰበት በወ/ሕ/ቁ 32(1)(ሀ)፣ 34(1)(3) እና 693(1) ስር ጥፋተኛ በማድረግ ቅጣትን በተመለከተ አመልካች የወንጀል ሪከርድ የሌለበት መሆኑን፣ የቤተሰብ አስተዳዳሪ፣ የጤና እክል ያለበት ታማሚ መሆኑን፣ በተለያየ የበጎ አድራጎት ስራ ላይ የሚሳተፍ መሆኑንና በችሎት ላይ መልካም ስነ ምግባር የሚያሳይ በመሆኑ 5 የቅጣት ማቅለያ በመያዝ በመነሻነት ከተያዘው ከእርከን 25 ወደ እርከን 20 ዝቅ በማድረግ በአራት አመት ከአምስት ወር ፅኑ እስራት እና አስር ሺህ ብር የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ የፅኑ እስራት ቅጣትን በተመለከተ ከባድ የስኳር፣ የነርቭ እና የደም ግፊት በሽታ ያለበት የቤተሰቡን አባል በራሱ ገንዘብ የሚያስተዳድር ሰፊ የኢንቨስትመንት ስራ በማካሄድ ለብዙ ሰራተኞች የስራ እድል የፈጠረ በመሆኑ ቅጣቱ እንዲገደብለት በመጠየቁ የእስራት ቅጣት ቢፈፀም በቤተሰቡ እና እያካሄደ ባለው የኢንቨስትመንት ስራ ላይ ጉዳት የሚደርስበት በመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር መዝገብ ቁጥር 177216 ቅፅ 24 ላይ በሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሰረት የተወሰነበት የፅኑ እስራት ቅጣት ሳይፈፀም በወ/ህ አንቀፅ 192 እና 194(1)(ለ) መሰረት በሁለት አመት ገድቦታል፡፡

ተጠሪ በዚህ በገደብ ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቅሬታ አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 355844 በቀን 22/09/2016 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተጠሪ 5 የቅጣት ማቅለያ ሊያዝለት አይገባም ሊያዝ የሚገባው 4 የቅጣት ማቅለያ ብቻ ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት መልካም ስነ ምግባር አሳይቷል በማለት አንድ የቅጣት ማቅለያ መያዙ በማስረጃ ያልተደገፈ ስለሆነ በስር ፍርድ ቤት የተያዘው 5ኛ የቅጣት ማቅለያ ምክንያትን ውድቅ በማድረግ ከእርከን 20 ወደ እርከን 21 ከፍ በማድረግ ቅጣቱን ወስኖ የእስራት ገደቡን በማንሳት የፅኑ እስራት ቅጣት እንዲፈፀም እንዲወሰን በማለት ተጠሪ ያቀረበውን ቅሬታ መርምሮ በስር ፍርድ ቤት ለአመልካች የተያዘለት 5 የቅጣት ማቅለያ መያዙ አግባብ ነው በማለት የተጠሪን ቅሬታ ውድቅ ካደረገ በኃላ ገደብን በተመለከተ አመልካች ከግል ተበዳይ ጋር ያልታረቀ ወይም ገንዘቡን ለመክፈል ፍቃደኛ ያልሆነ ስለሆነ የፅኑ እስራት ቅጣት መገደቡ አግባብ አይደለም በማለት ገደቡን በማንሳት በስር ፍርድ ቤት የተወሰነውን የአራት አመት ከአምስት ወር ፅኑ እስራት እንዲፈፀም ሲል ወስኗል፡፡ የአሁን አመልካች በዚህ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሰበር አቤቱታ ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

የአሁን የሰበር ቅሬታ የቀረበው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎት በሰጡት ውሳኔ እና ትዕዛዝ ላይ ቅር በመሰኘት ነው፡፡ አመልካች በ 13/10/2016 ዓ.ም 04 ገፅ የሰበር አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን ይዘቱም በአጭሩ ኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በራሱ አነሳሽነት በማንሳት የእስራት ቅጣት እንዲፈፀም መወሰኑ ስህተት ነው፡፡ ተጠሪ የጠየቀው ዳኝነት አንድ የቅጣት ማቅለያ ውድቅ ሆኖ 4 የቅጣት ማቅለያ ብቻ ተይዞ የእስራት ቅጣት ገደብ እንዲነሳ የሚል ሆኖ እያለ ፍርድ ቤቱ ስር ፍርድ ቤት የያዘውን 5 የቅጣት ማቅለያዎች እንዳለ ከወሰደ በኃላ 4 አመት ከ 5 ወር ፅኑ እስራት ቅጣት እንዲፈፀም ማለቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፡፡ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት የጠየቀው ዳኝነት ጥያቄ ከ 5 የቅጣት ማቅለያዎች መካከል ጥሩ ስነ ምግባር ስለመኖሩ ማስረጃ ሳያቀርብ ጥሩ ስነ ምግባር አለው ተብሎ የተያዘው አንድ የቅጣት ማቅለያ ተነስቶ 4 የቅጣት ማቅለያ ብቻ ሲያዝ ቅጣቱ ከእርከን 20 ወደ 21 ከፍ ስለሚል በእርከን 21 ስር ቅጣቱ ከ 5 አመት በላይ በመሆኑ ከ 5 አመት በላይ ፅኑ እስራት ቅጣት በሚሆንበት ጊዜ ህጉ እንዲገደብ ስለማይፈቅድ ገደቡ ተነስቶ ቅጣቱን እንዲፈፅም በማለት ጠይቆ ፍርድ ቤቱ የተጠሪን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ በስር ፍርድ ቤት የተያዘው 5 የቅጣት ማቅለያ መያዙ አግባብ መሆኑን ከተቀበለ በኃላ ተጠሪ ከጠየቀው ጥያቄ ውጭ ቅጣቱን ሳያሻሽል 4 አመት ከ 5 ወር ፅኑ እስራት እንዲፈፀም የተሰጠው ገደብ እንዲነሳ መወሰኑ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ነው፡፡

ከፍተኛ ፍርድ ቤት በወ/ህ አንቀፅ 192 እና 194 መሰረት እስራት ቅጣቱን ሊገደብ የቻለው መሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች ስለተሟላ ነው፡፡ የእስራት ቅጣት ለመገደብ በወ/ህ አንቀፅ 192 እና 194 መሰረት ከግል ተበዳይ ጋር መታረቅ ወይም ገንዘብ መክፈል እንዳለበት የሚያስገድድ አይደለም፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 185700 በተመሳሳይ ጉዳይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠበት ስለሆነ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ ይህን የሰበር ውሳኔ የሚጣረስ ስለሆነ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ተሽሮ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲፀናልኝ የሚል ነው፡፡

ይህ ሰበር ችሎት የገደብ ጥያቄ በስር ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውድቅ መደረጉን ከወ/ህ አንቀፅ 192 እና ተከታታይ ድንጋጌዎች እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 171403፣ 177216 እና 185700 ከሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም አንፃር ተገቢ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ሲባል በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 2(4)(ሸ) እና 10(1)(ሐ) እንዲሁም በሰበር ስነ ስርአት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 7(3) መሰረት ተጠሪ በጉዳዩ ላይ መልስ እንዲሰጥበት ታዞ ተጠሪ በቀን 16/03/2017 ዓ.ም በ 03 ገፅ መልሱን አቅርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!

ይዘቱ በአጭሩ በስር ፍርድ ቤት ማስረጃ ሳይቀርብ ስነ ምግባሩ ጥሩ ነው ተብሎ የተያዘው አንድ የቅጣት ማቅለያ ቢነሳ ቅጣቱ እርከን 21 ስር ስለሚያርፍ እርከን 21 ስር ቅጣቱ ከ 5 አመት በላይ ስለሚሆን ከ 5 አመት በላይ ቅጣት ሊገደብ የማይችል መሆኑን አመልካች ከግል ተበዳይ ጋር ሳይታረቅ እና ገንዘቡን ሳይከፍል እስራት ቅጣቱን መገደብ አግባብ ያለመሆኑን በመረዳት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔን በማሻሻል የገደብ ውሳኔውን በማንሳት ፅኑ እስራት ቅጣቱን እንዲፈፅም መወሰኑ አግባብ ስለሆነ እንዲያፀናልኝ የሚል ነው፡፡

አመልካች የመልስ መልሱን በ 30/03/2017 ዓ.ም በ 02 ገፅ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር አቅርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ በተገለፀው መሰረት የተጠቃለለ በመሆኑ እኛም ለዚህ ሰበር ቅሬታ መነሻ የሆነው ውሳኔ በግራ ቀኙ በኩል ከቀረበው ክርክር፣ ይህ ሰበር ችሎት ካስቀረበው ጭብጥ አንፃር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የገደብ ውሳኔውን በማንሳት ፅኑ እስራት ቅጣቱን አመልካች ሊፈፅም ይገባል በማለት የደረሰበት ድምዳሜ ተገቢ መሆን አለመሆኑን ከወ/ህ አንቀፅ 192 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች እና ከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 171403፣ 177216፣ 185700 ከሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም አንፃር እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር አገናዝበን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

መርምረን እንደተረዳነው ከሆነ በስር ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ ተጠሪ ያቀረበው ክስ የወ/ሕ አንቀፅ 32(1)(ሀ)፣ 34(1) እና 693(1) በመተላለፍ ለግል ተበዳይ አቶ ሽምሱ አወል የብር አምስት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሺህ ብር ከኦሮሚያ ህብረት ባንክ የሚመነዘር ቼክ ሰጥቶ የግል ተበዳይ ገንዘቡን ለማውጣት ወደ ባንክ ሲሄድ በቂ ገንዘብ የለውም በመባሉ ገንዘቡን ሊወስድ አልቻለም፡፡ ስለዚህ በቂ ስንቅ ሳይኖር ቼክ በማውጣት ወንጀል ተከሷል የሚል ሲሆን አመልካች ክሱን ክዶ በመከራከሩ የስር ፍርድ ቤት የተጠሪን የሰውና የሰነድ ማስረጃ ከሰማ በኃላ አመልካች እንዲከላከል ብይን ሰጥቶ የአመልካችን የመከላከያ ማስረጃ ከሰማ በኃላ አመልካች በመከላከያ ምስክሩ የተጠሪን የሰውና የሰነድ ማስረጃ አላስተባበለም በማለት አመልካች በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ በማድረግ 5 የቅጣት ማቅለያ በመያዝ በ 4 አመት ከ 5 ወር ፅኑ እስራት እና አስር ሺህ ብር የገንዘብ መቀጫ ቅጣት ወስኗል፡፡

የፅኑ እስራት ቅጣት አፈፃፀምን በተመለከተ ከባድ የስኳር፣ የነርቭ እና የደም ግፊት በሽታ መኖሩን፣ የቤተሰቡን አባል በራሱ ገቢ የሚያስተዳድር መሆኑን፣ ሰፊ የኢንቨስትመንት ስራ በመስራት ለብዙ ሰራተኞች የስራ እድል የፈጠረ በመሆኑ ቅጣቱ እንዲገደብለት የጠየቀ በመሆኑ የፅኑ እስራት ቅጣቱ ቢፈፀም በቤተሰቡ እና እየሰራ ባለው የኢንቨስትመንት ስራ ላይ ጉዳት የሚያደርስ በመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 177216 ቅፅ 24 ላይ ከሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሰረት

የተወሰነበት የፅኑ እስራት ቅጣት ሳይፈፀም በወ/ህ አንቀፅ 192 ቅጣቱ ሳይፈፀም በሁለት አመት ገደብ ታግዶ እንዲቆይ ወስኗል፡፡ ተጠሪ በይግባኝ ሰሚ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያነሳው ክርክር ከፍተኛ ፍርድ ቤት 5 የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን ይዞ ቅጣቱን የገደበው አግባብ አይደለም፡፡ የአመልካች ስነ ምግባር ጥሩ ነው ተብሎ የተያዘለት አንድ የቅጣት ማቅለያ ስነ ምግባሩ ጥሩ መሆኑ በማስረጃ ሳይረጋገጥ የተያዘ በመሆኑ ይህ ያለአግባብ የተያዘው አንድ የቅጣት ማቅለያ ሲነሳ በእርከን 21 ስር ቅጣቱ ከ 5 አመት በላይ በመሆኑ የገደብ ውሳኔው እንዲነሳ የሚል ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አንድ የቅጣት ማቅለያ ሊይዝ አይገባም በማለት ያነሳውን ቅሬታ አልተቀበለውም፡፡

ገደብ ጥያቄን በሚመለከት ተጠሪ አንድ የቅጣት ማቅለያ የተያዘው ውድቅ ተደርጎ አራት የቅጣት ማቅለያ ብቻ ተይዞ ከእርከን 20 ወደ እርከን 21 ከፍ ተደርጎ ፅኑ እስራት ቅጣት ከ 5 አመት በላይ ስለሆነ ገደብ ተነስቶ ቅጣቱን እንዲፈፅም እንዲወሰን ጠይቆ እያለ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት 5 ቅጣት ማቅለያ የተያዘው በአግባቡ መሆኑን ከተቀበለ በኋላ ቅጣቱንም ሲያሻሽል አመልካች ከግል ተበዳይ ጋር አልታረቀም ገንዘቡንም ለመክፈል መተማመኛ አልሰጠም በማለት ገደቡ ተነስቶ የ 4 አመት ከ 5 ወር ፅኑ እስራት እንዲፈፀም የወሰነበት ሁኔታን ስንመለከት ተጠሪ ከጠየቀው ዳኝነት ጥያቄ በመውጣት በራሱ አነሳሽነት ያልተጠየቀ ዳኝነት የሰጠ መሆኑን ከመዝገቡ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ቅጣቱ ሊገደብ አይገባም የሚልበት ምክንያት አመልካች ከግል ተበዳይ ጋር አልታረቀም ገንዘቡንም አልከፈለም ከሚል መነሻ ነው፡፡ ቅጣቱን ለመገደብ ከግል ተበዳይ ጋር መታረቅ ገንዘብ መክፈል ግዴታ ሆኖ በህጉ ውስጥ አልተደነገገም፡፡

በወንጀል ህግ አንቀፅ 192 ስር ጥፋተኛው አስቀድሞ የተፈረደበት ቢሆንም ባይሆንም በአንቀፅ 194 የተፈረደበትን ቅጣት ከመፈፀሙ በፊት ለተወሰነ ጊዜ ቅጣቱ ታግዶለት አመሉ ቢፈተን ሁለተኛ ጥፋት ከማድረግ የሚታገድ መሆኑንና ስለጠባዩም መሻሻል አንድ ፅኑ ማስጠንቀቂያ ብቻ የሚበቃ መሆኑን ፍርድ ቤቱ ያመነበት እንደሆነ ቅጣቱን ከወሰነ በኃላ የተወሰነ የፈተና ጊዜ በመስጠት የቅጣቱ አፈፃፀም ታግዶ እንዲቆይ ሊያዝ ይችላል በማለት ይደነግጋል፡፡ በዚህ ድንጋጌ ስር አመልካች ከግል ተበዳይ ጋር መታረቀ እና ገንዘቡን መክፈል እንዳለበት መስፈርት አልተቀመጠም፡፡ ቅጣቱ ከመፈፀሙ በፊት ለተወሰነ ጊዜ ቅጣቱ ታግዶለት አመሉ ቢፈተን ሁለተኛ ጥፋት ከማድረግ የሚታገድ መሆኑንና ስለ ጠባዩም መሻሻል አንድ ፅኑ ማስጠንቀቂያ ብቻ የሚበቃ መሆኑን ፍርድ ቤቱ ያመነ እንደሆነ ቅጣቱን ሊገድብ እንደሚችል የሚገልፅ በመሆኑ ይህ ድንጋጌ ስልጣኑን ለዳኛው የሰጠ ከመሆኑም ሌላ ስለ እርቅ እና ካሳ ተቀጪው አስቀድሞ ሊከፍል ይገባል የሚል አይደለም፡፡

በዚህ ድንጋጌ መሰረት ስለሚሰጥ ስለ ገደብ ጥያቄ በተመለከተ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 185700 ላይ በሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም ከግል ተበዳይ ጋር ታርቆ ካሳ መክፈል በወንጀል ህጉ አንቀፅ 197 መሰረት ጥፋተኛው በተሰጠው የፈተና ጊዜ ውስጥ በመልካም ጠባይ እንዲመራ እና በፈተና ጊዜ ውስጥ ተገቢውን ፍሬ እንዲያፈራ በሚል ለመልካም ጠባይ አመራር ዋስትና

የሚሰጥ ትዕዛዝ እንጂ ቅጣትን ለመገደብ ቅድመ ሁኔታዎች እንዳልሆኑ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ ቅጣት የማይገደብባቸው ምክንያቶች በወ/ህ አንቀፅ 194 ስር ተደንግጓል፡፡

የተጠሪ ክርክር በስር ፍርድ ቤት የተያዘው አንድ የቅጣት ማቅለያ ባይያዝ ኖሮ ቅጣቱ ከ 5 አመት በላይ ስለሚሆን ቅጣቱ እንዲገደብ ህጉ አይፈቅድም የሚል ክርክር ሲሆን የስር ፍርድ ቤት የተጠሪን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ 5 የቅጣት ማቅለያ መያዙ እና 4 አመት ከ 5 ወር ፅኑ እስራት አግባብ መሆኑን ከተቀበለ በኃላ በወ/ህ አንቀፅ 192 ስር ቅጣቱን ለመገደብ ያልተቀመጡ ምክንያቶችን በመዘርዘር አመልካች ከግል ተበዳይ ጋር ታርቆ ገንዘቡን አልከፈለም የሚል ምክንያት በመስጠት በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠው ገደብ እንዲነሳ መወሰኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 185700 ላይ ከሰጠው የህግ ትርጉም ጋር የሚጣረስ ውሳኔ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡

ሲጠቃለል የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ 4 አመት ከ 5 ወር ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ከወሰነ በኃላ ቅጣቱን በተመለከተ አመልካች የቤተሰብ አስተዳዳሪ፣ በኢንቨስትመንት ስራ ለብዙ ሰራተኞች የስራ እድል የፈጠረ እንዲሁም ለመንግስትም ከፍተኛ የኢኮኖሚ ጥቅም የሚያስገኝ መሆኑን በመገመት ቅጣቱ በወ/ህ አንቀፅ 192 መሰረት ሳይፈፀም በሁለት አመት ታግዶ እንዲቆይ መወሰኑ በህጉ ላይ የተደነገገ ድንጋጌ ሆኖ እያለ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች ከግል ተበዳይ ጋር ታርቆ ገንዘብ አልከፈለም የሚል ምክንያት በመጥቀስ ከተጠሪ በኩል ስለ እርቅ ጉዳይ ክርክር ሳይቀርብ በራሱ አነሳሽነት ያልተጠየቀ ዳኝነት በመስጠት ቅጣቱ እንዳይገደብ የሚከለክል ምክንያት ሳይኖር በከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠው ገደብ ተነስቶ አመልካች ፅኑ እስራት ቅጣቱን እንዲፈፅም መወሰኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 185700 በቀን 30/06/2013 ዓ.ም የሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉምን የሚጣረስ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 2(4)(ሸ) እና 10(1)(ሐ) መሰረት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 355844 በቀን 22/09/2016 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 454355 በቀን 26/09/2016 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስነ ስርአት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9(1)(ለ) መሰረት ተሽሯል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!

2. የሸገር ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 74523 በቀን 07/11/2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስነ ስርአት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 9(1)(ሀ) መሰረት ፀንቷል፡፡
3. ጉዳዩ እልባት ያገኘ በመሆኑ አመልካች ለዋስትና በዚህ ችሎት በ 28/02/2017 ዓ.ም ያስያዘው ብር 20,000.00 (ሃያ ሺህ ብር) በሞዴል 85 ካርኒ ቁጥር 0173730 ያስያዘው ገንዘብ እንዲለቀቅ ብለናል፡፡
4. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡

**<u>ትዕዛዝ</u>**

- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

**<u>ማስታወሻ</u>፡** - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም!